# ፍትሐ ነገሥት
# ንባቡና ትርጓሜው

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ
ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት በሆኑ
በ፮ኛው ዓመት ለ፫ኛ ጊዜ ታተመ ።

አሳታሚ
ትንሣኤ የመጻሕፍት ማሳተሚያ ድርጅት
አዲስ አበባ ፲፱፻፺ ዓ·ም



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት

## መግቢያ፡—

ፍትሐ ነገሥት የሚው ቃል "ፍትሕ እና ነገሥት" በሚሉት ሁለት ቃላት የተሰናሰለ ወይም የተያያዘ ቃል ነው ። ትርጓሜውም ፍርድ ፣ ውሳኔን መስጠት፣ ሕግና ሥርዓትን ማስፈን ማለት ሲሆን ነገሥታቱ ክርስቲያኖች ከመሆናቸው ጋር ሥጋዊውንም ሆነ መንፈሳዊውን ፍትሕ ይመለከቱ ስለነበር በነገሥታቱ ስም "ፍትሐ ነገሥት" ተብሎ ተሰይሞአል ። ኢትዮጵያ አገራችን በጽሑፍ ከአሉዋት ጥንታውያን የሕግ መጻሕፍት መካከል ታላቁና የታወቀው ፍትሐ ነገሥት የተባለው መጽሐፍ ነው ።

ፍትሐ ነገሥት ከዓረብኛ ወደ ግእዝ የተተረጐመውና በሥራ ላይ የዋለው በንጉሠ ነገሥቱ አፄ ዘርዐያቆብ (ከ1444 እስከ 1468) ዓ.ም እንደሆነ ይታወቃል ። ከዚህም ጋር ይህ የሕግና የሥርዓት መጽሐፍ በመላ ኢትዮጵያ ተዳርሶ ሊቃውንቱ እየተማሩትና እያስተማሩት በሕግ ሸንጐ ላይ ሊውል ችሎአል ። ሊቃውንቱ ለአያሌ ዘመናት በብራና ብቻ በእጅ እየጻፉ ፣ በጉባዔ እየተረጐሙ ትምህርቱ ከአንዱ ወደ አንዱ በቃል እየተላለፈ በኢትዮጵያም የሕግ ቀዋሚ የፍርድ መጽሐፍ ሆኖ አገልግሎአል ። በተለይ ይህን መጽሐፍ ለሚያውቁ የሕግ ሊቃውንት ሁሉ ከፍተኛ የሕግ አዋቂነት የመዓርግ ስም ይሰጣቸው ነበር ። የፍትሐ ነገሥት መጽሐፍ በሀገራችን ሥርወ ሕግ ሁኖ ብዙ ዘመን የተሠራበት ከመሆኑ ጋር አሁንም የሕግ ምንጭነቱን እንደያዘ ይገኛል ።

በመሠረቱ ፍትሐ ነገሥት ፍትሕ መንፈሳዊና ፍትሕ ሥጋዊ ፣ ተብሎ በሁለት ዐበይት ክፍሎች የተከፈለ ነው ። በ1948 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ተረቆ በአዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በኢትዮጵያችን ይሠራበት የነበረው ሕግ ፍትሐ ነገሥት እንደነበር ግልጽ ነው ። መንፈሳዊ ሕግነቱም አሁንም በሥራ ላይ እንደዋለ ነው። በመሆኑም

1ኛ/ በ1956 ዓ.ም በግዕዝ ብቻ

2ኛ/ በ1958 ዓ.ም ንባብና ትርጓሜው

3ኛ/ በ1961 ዓ.ም በእንግሊዝኛ

4ኛ/ መጽሐፈ ሕግጋት ዐበይት በሚል ስያሜ በ1962 ዓ.ም በግእዝና በአማርኛ ታትሞ በሥራ ላይ ውሎአል ። ሆኖም የመጽሐፉ አገልግሎት እጅግ በጣም አስፈላጊ በመሆኑና ቀደም ሲል የታተመው ተሠራጭቶ በማለቁና የምእመናኑም ፍላጐትና ጥያቄ በርካታ በመሆኑ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ፣ ፓትርያርክ ፣ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት በሆኑ በ፷ኛው ዓመት እነሆ በግእዝና በአማርኛ ለ5ኛ ጊዜ አሳትመን ማቅረባችንን ስናበስር መንፈሳዊ ደስታ ይሰመናል ።

"ወስብሐት ለእግዚአብሔር"

ማሳተሚያ ድርጅቱ

fteha/04

# ማ ው ጫ

ገጽ

## አንቀጽ ፡ ቀዳማዊ ።


፩. በእንተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወበእንተ ፡ ኵሉ ፡ ዘይደሉ ፡ ላቲ ፡ . . . . . . . . . . ፳፩
፪. በእንተ ፡ ጥንተ ፡ መጻሕፍት ፡ ውኩፋት ፡ . . . . ፳፫
፫. በእንተ ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ ወበእንተ ፡ እለ ፡ ይበውኡ ፡ ውስተ ፡ ሃይማኖት ፡ . . . . . . . . . . ፳፬
፬. በእንተ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ . . . . . . . . . . ፳፰
፭. በእንተ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ . . . . . . . . . . ፴፯
፮. በእንተ ፡ ቀሳውስት ፡ . . . . . . . . . . ፵
፯. በእንተ ፡ ዲያቆናት ፡ . . . . . . . . . . ፵፯
፰. በእንተ ፡ እለ ፡ ተርፉ ፡ ላዕካነ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ . . . . . . . . . . ፶፫
፱. በእንተ ፡ ኵሎሙ ፡ ካህናት ፡ . . . . . . . . . . ፶፮
፲. በእንተ ፡ መነኮሳት ፡ ወመነኮሳይያት ፡ . . . . . ፻፫
፲፩. በእንተ ፡ ተግሣጽ ፡ ወትእዛዘ ፡ ሕዝብ ፡ . . . . ፻፳፪
፲፪. በእንተ ፡ ቅዳሴ ፡ . . . . . . . . . . ፻፴፫
፲፫. በእንተ ፡ ቍርባን ፡ . . . . . . . . . . ፻፴፰
፲፬. በእንተ ፡ ጸሎት ፡ . . . . . . . . . . ፻፵፪
፲፭. በእንተ ፡ ጾም ፡ . . . . . . . . . . ፻፶
፲፮. በእንተ ፡ ምጽዋት ፡ . . . . . . . . . . ፻፶፯
፲፯. በእንተ ፡ ዘይሠየም ፡ ለከፊለ ፡ ምጽዋት ፡ . . . ፻፷፰
፲፰. በእንተ ፡ አሥራት ፡ ወበኵራት ፡ ወብጽዓታት ፡ ወጕልታት ፡ . . . . . . . . . . ፻፸፪
፲፱. በእንተ ፡ እሑዳት ፡ በዓላት ፡ . . . . . . . . . . ፻፹
፳. በእንተ ፡ ሰማዕታት ፡ ወተአማንያን ፡ ወከሐድያን ፡ . . . . . . . . . . ፻፹፯
፳፩. በእንተ ፡ ድዉያን ፡ . . . . . . . . . . ፻፺፪
፳፪. በእንተ ፡ ሙታን ፡ . . . . . . . . . . ፻፺፫


## ክፍል ፡ ዳግማዊ ።

በእንተ ፡ ግብራት ፡ ዓለማውያት ፡ ዘምግብና ፡


፳፫. በእንተ ፡ መባልዕት ፡ ወአልባሳት ፡ ወአብያት ፡ ወተግባራት ፡ . . . . . . . . . . ፻፺፰
፳፬. በእንተ ፡ ሕፀ ፡ ወውሂበ ፡ ንዋይ ፡ ዘእቅም ፡ ሰብሳብ ፡ ወአውሰቦ ፡ . . . . . . . . . . ፪፻፯
፳፭. በእንተ ፡ ሕርመት ፡ ዕቁባት ፡ . . . . . . . . . . ፪፻፵፪
፳፮. በእንተ ፡ ሀብት ፡ . . . . . . . . . . ፪፻፵፫
፳፯. በእንተ ፡ ልቃሕ ፡ ወተሐብዮ ፡ ወእኀዝ ፡ ወአመግቦ ፡ . . . . . . . . . . ፪፻፵፯
፳፰. በእንተ ፡ ሕስት ፡ ከመ ፡ ልብስ ፡ ወእንስሳ ፡ ወካልእኒሆሙ ፡ . . . . . . . . . . ፪፻፶፩
፳፱. በእንተ ፡ ምቅብና ፡ ንዋይ ፡ ወዘይመስሎ ፡ . . ፪፻፶፭


## መጀመሪያ ፡ አንቀጽ ።


፩. ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ ለሷም ፡ ስለሚገባው ፡ ሁሉ ፡ . . . . . . . . . . ፳፩
፪. ስለ ፡ ሚቀበሏቸው ፡ ጥንታውያን ፡ መጻሕፍት ፡ ፳፫
፫. ስለ ፡ ክርስትናና ፡ ጥምቀትም ፡ ወደ ፡ ሃይማኖት ፡ ስለሚገቡ ፡ ሰዎች ፡ . . . . . . . . . . ፳፬
፬. ስለ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ . . . . . . . . . . ፳፰
፭. ስለ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ . . . . . . . . . . ፴፯
፮. ስለ ፡ ቀሳውስት ፡ . . . . . . . . . . ፵
፯. ስለ ፡ ዲያቆናት ፡ . . . . . . . . . . ፵፯
፰. ስለ ፡ ቀሩት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልጋዮች ፡ . . . . . . . . . . ፶፫
፱. ስለ ፡ ካህናት ፡ ሁሉ ፡ . . . . . . . . . . ፶፮
፲. ስለ ፡ መነኮሳትና ፡ መነኮሳይያት ። . . . . . . . . ፻፫
፲፩. ስለ ፡ ተግሣጽና ፡ ስለ ፡ ሕዝብ ። . . . . . . . . ፻፳፪
፲፪. ስለ ፡ ቅዳሴ ፡ . . . . . . . . . . ፻፴፫
፲፫. ስለ ፡ ቍርባን ፡ . . . . . . . . . . ፻፴፰
፲፬. ስለ ፡ ጸሎት ፡ . . . . . . . . . . ፻፵፪
፲፭. ስለ ፡ ጾም ፡ . . . . . . . . . . ፻፶
፲፮. ስለ ፡ ምጽዋት ፡ . . . . . . . . . . ፻፶፯
፲፯. ምጽዋትን ፡ ለመክፈል ፡ ስለሚሾም ፡ . . . . ፻፷፰
፲፰. ስለ ፡ አሥራትና ፡ ስለ ፡ በኵራት ፡ ስለ ፡ ሥዕለቶችና ፡ ስለ ፡ ጕልቶች ። . . . . . . . . ፻፸፪
፲፱. ስለ ፡ እሑዶችና ፡ ስለ ፡ በዓላት ፡ . . . . . . . . . ፻፹
፳. ስለ ፡ ሰማዕታትና ፡ አማንያን ፡ እንዲሁም ፡ ከሐድያን ። . . . . . . . . . . ፻፹፯
፳፩. ስለ ፡ በሽተኞች ፡ . . . . . . . . . . ፻፺፪
፳፪. ስለ ፡ ሙታን ፡ . . . . . . . . . . ፻፺፫


## ሁለተኛ ፡ ክፍል ።

ስለ ፡ ዓለማውያን ፡ ሥራና ፡ አስተዳደር ፡


፳፫. ስለ ፡ ምግቦችና ፡ ስለ ፡ ልብሶች ፡ ስለ ፡ ቤቶችና ፡ ስለ ፡ ሥራዎች ። . . . . . . . . . . ፻፺፰
፳፬. ስለ ፡ መተጫጨትና ፡ ስለማጫ ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ ጋብቻም ። . . . . . . . . . . ፪፻፯
፳፭. ዕቁባትን ፡ ስለ ፡ መተው ፡ . . . . . . . . . . ፪፻፵፪
፳፮. ስለ ፡ ሀብት ፡ . . . . . . . . . . ፪፻፵፫
፳፯. ስለ ፡ ብድርና ፡ ስለ ፡ ዋስትና ፡ ስለ ፡ መያዣ ፡ ስለ ፡ መጋቢነት ፡ . . . . . . . . . . ፪፻፵፯
፳፰. እንደ ፡ ልብስና ፡ እንደ ፡ እንስሳት ፡ ሌሎቹንም ፡ ስለ ፡ መስሉ ፡ መያዣ ፡ . . . . . . . . . . ፪፻፶፩
፳፱. ገንዘብን ፡ አደራ ፡ ስለ ፡ ማስጠበቅና ፡ ስለ ፡ መስለውም ፡ . . . . . . . . . . ፪፻፶፭

፴. በእንተ ፡ ምግብና ፡ ................ ፪፻፶፱
፴፩. በእንተ ፡ ግብርናት ፡ ወግእዛን ፡ ወአግእዞ ፡
ግብር ፡ ...................... ፪፻፷፩
፴፪. በእንተ ፡ ሐፃኒ ፡ ዘከመ ፡ ሕቅፈት ፡ ሕፃን ፡
በኵሉ ፡ ግብሩ ፡ .................. ፪፻፷፫
፴፫. በእንተ ፡ ሌዋ ፡ ወተማይጦ ፡ ወመትሎሙ ፡ ፪፻፷፱
፴፬. በእንተ ፡ ተሳትፎ ፡ ንዋይ ፡ ወዘይመስሎ ፡
ለዝንቱ ፡ ግብር ፡ .................. ፪፻፸
፴፭. በእንተ ፡ አገብሮ ፡ ወመዓት ፡ ......... ፪፻፸፪
፴፮. በእንተ ፡ ተአስቦ ፡ ቤት ፡ ወውሂበ ፡ ንዋይ ፡
ለምድር ፡ ዘከመ ፡ ገመታ ፡ ........... ፪፻፸፯
፴፯. በእንተ ፡ ሐኒጸ ፡ ሕንፃ ፡ ወዘይተልዎ ፡ ... ፪፻፹፪
፴፰. በእንተ ፡ ልቃሕ ፡ .................... ፫፻፪
፴፱. በእንተ ፡ ተአምኖ ፡ ኀጣውእ ፡ .......... ፫፻፫
፵. በእንተ ፡ ረኪበ ፡ ዘተንድፈ ፡ እምእንስሳ ፡
ዘይመስሎ ፡ ...................... ፫፻፯
፵፩. በእንተ ፡ ጽሒፈ ፡ ትእዛዝ ፡ በንዋይ ፡ ..... ፫፻፲፩
፵፪. በእንተ ፡ ርስት ፡ .................. ፫፻፳፯
፵፫. በእንተ ፡ ፈታሒ ፡ ወዘምስሌሁ ፡ ...... ፫፻፴፯
፵፬. በእንተ ፡ ነገሥት ፡ ................. ፫፻፵፯
፵፭. በእንተ ፡ ብሉይ ፡ ወሐዲስ ፡ ......... ፫፻፸፭
፵፮. በእንተ ፡ ኵነኔ ፡ ከሐድያን ፡ ........... ፬፻፩
፵፯. በእንተ ፡ ቀታልያን ፡ ................ ፬፻፯
፵፰. በእንተ ፡ ተግሣጸ ፡ ዝሙት ፡ ......... ፬፻፲፯
፵፱. በእንተ ፡ ኵነኔ ፡ ሰረቅት ፡ ........... ፬፻፳፭
፶. በእንተ ፡ ኑልቈ ፡ ኀጣውእ ፡ .......... ፬፻፳፯
፶፩. በእንተ ፡ ዘዚአሁ ፡ ኍልቈ ፡ ምግባራት ፡ .. ፬፻፴፪

፴. ስለ ፡ መጋቢነት ፡ ................ ፪፻፶፱
፴፩. ስለ ፡ ባርነትና ፡ ስለ ፡ ነፃነት ፡ ባሪያንም ፡ ነፃ ፡
ስለ ፡ ማውጣት ፡ ................. ፪፻፷፩
፴፪. ስለ ፡ ሞግዚት ፡ በሥራ ፡ ሁሉ ፡ ሕፃንን ፡ እንደ ፡
ማሳደግ ፡ ...................... ፪፻፷፫
፴፫. ስለ ፡ ዋጋና ፡ ስለመገበያየት ፡ ስለ ፡
ሚከተላቸውም ፡ ................ ፪፻፷፱
፴፬. በገንዘብ ፡ ሽርክ ፡ ስለ ፡ መሆንና ፡ ይህንም ፡
ስለሚመስለው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ........ ፪፻፸
፴፭. ግድ ፡ ስለ ፡ ማለትና ፡ ስለ ፡ መቆጣት ፡ ... ፪፻፸፪
፴፮. ቤትን ፡ ስለ ፡ መከራየትና ፡ ለመሬት ፡ ገንዘብን ፡
ስለ ፡ መስጠት ፡ ................. ፪፻፸፯
፴፯. ሕንፃን ፡ ስለ ፡ መሥራትና ፡ ስለ ፡
ሚከተለውም ፡ .................. ፪፻፹፪
፴፰. ስለ ፡ ብድር ፡ ................... ፫፻፪
፴፱. ኃጢአትን ፡ ስለ ፡ መታመን ፡ ......... ፫፻፫
፵. ከእንስሳው ፡ ወገን ፡ የጠፋውን ፡
ለማግኘትና ፡ ስለሚመስለውም ፡ ...... ፫፻፯
፵፩. በገንዘብ ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡ መጻፍ ፡ ....... ፫፻፲፩
፵፪. ስለ ፡ ርስት ፡ ................... ፫፻፳፯
፵፫. ስለ ፡ ዳኛና ፡ እርሱን ፡ ስለመሰለው ፡ .... ፫፻፴፯
፵፬. ስለ ፡ ነገሥት ፡ .................. ፫፻፵፯
፵፭. ስለ ፡ ብሉይና ፡ ሐዲስ ፡ ........... ፫፻፸፭
፵፮. ስለ ፡ ከሐድያን ፡ ፍርድ ፡ ........... ፬፻፩
፵፯. ስለ ፡ ነፍስ ፡ ገዳዮች ፡ .............. ፬፻፯
፵፰. ስለ ፡ ዝሙት ፡ ቅጣት ፡ ............ ፬፻፲፯
፵፱. ስለ ፡ ሌብነት ፡ ፍርድ ፡ ............ ፬፻፳፭
፶. ስለ ፡ ኃጢአት ፡ ቍጥር ፡ ........... ፬፻፳፯
፶፩. ስለ ፡ እያንዳንዱ ፡ የሥራዎች ፡ ቍጥር ፡ ... ፬፻፴፪

በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ቅዱስ ፡ አሐዱ ፡ አምላክ ፡ ንዌጥን ፡ በረድኤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወሠናይ ፡ ሠርሖቱ ፡ በጽሒፈ ፡ መቅድመ ፡ ጉባኤ ፡ ዘአስተጋብእዎ ፡ ሊቃውንት ፡ ጸሎቶሙ ፡ ወበረከቶሙ ፡ ወሀብተ ፡ ረድኤቶሙ ፡ የሀሉ ፡ ምስለ ፡ ኵሎሙ ፡ ክርስቲያን ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ ፩ ፡ አምላክ ፤ ሊቃውንት ፡ የሰበሰቡትን ፡ የዚህን ፡ መጽሐፍ ፡ መቅድም ፡ መጻፍን ፡ በእግዚአብሔር ፡ አጋዥነትና ፡ በማቅናቱ ፡ መበጀት ፡ እንጀምራለን ። ጸሎታቸውና ፡ በረከታቸው ፡ የረድኤታቸውም ፡ ሀብት ፡ ከክርስቲያኖች ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ ለዘለዓለሙ ፡ ይኑር ፡ አሜን ።

ወእምድኅረ ፡ ኅልቀ ፡ ዓመተ ፡ ሰማዕታት ፡ ሶበ ፡ ረሰይዎ ፡ ንጉሠ ፡ ፫፻፲፰ቱ ፡ ወጀቱ ፡ ርቱዓነ ፡ ሃይማኖት ፡ ለቈስጠንጢኖስ ፤ ውእቱሂ ፡ ይቤሎሙ ፡ እንስ ፡ ኢይፈቅድ ፡ መንግሥተ ፤ እስመ ፡ ፍኖተ ፡ ክርስቶስ ፡ ወፍኖተ ፡ ዓለም ፡ ካልእ ፡ ውእቱ ። ወፍኖቱስ ፡ ለክርስቶስ ፡ ወትእዛዙ ፡ ጥይቅት ፡ "ትቤ ፡ አፍቅሩ ፡ ጸላእተክሙ ፤ ወሠናየ ፡ ግበሩ ፡ ለእለ ፡ ይትዔገሉክሙ" ዘንተ ፡ ወዘይመስሎ ። እስመ ፡ ዛቲ ፡ ትእዛዝ ፡ ሕገ ፡ ትሩፋት ፡ ይእቲ ፡ ዳግሚት ፡ ትኤዝዝ ፡ ከመ ፡ ይትዓገሡ ፡ ወከመ ፡ ይፁሩ ፡ ወይሥረዩ ፡ ወያናሕስዩ ፤ ወያሠንዩ ፡ ለውሉደ ፡ ቢጽ ፡ ወያስተዓርይዎሙ ፡ በነፍሶሙ ። እፎ ፡ ይትከሀለኒ ፡ ከመ ፡ እፅርዕ ፡ ዘንተ ፡ ትእዛዘ ፤ ወከመ ፡ እእዝዝ ፡ ኵነኔ ፡ ወፈድየ ፡ ዕዳ ፡ በጊዜሁ ፡ ዘእንበለ ፡ ምሕረት ፡ ወተበቅሎ ፡ ለግፉዕ ፡ እምነ ፡ ገፋዒሁ ። እስመ ፡ ኵሉ ፡ ዘፍጹም ፡ ይደሉ ፡ በግብር ፡ ከመ ፡ ይሥዐሮ ፡ ለዘየሐጽጽ ፡ ወበእንተዝ ፡ ሠዐረቶ ፡ ሕገ ፡ እግዚእነ ፡ ለዘይቀድም ፡ እምኔሃ ። ለዛቲሰ ፡ ኢይደሉ ፡ ተሥዕሮታ ፤ እስመ ፡ እልቦ ፡ ዘይከብር ፡ እምኔሃ ። ለሊሃ ፡ ሕገ ፡ ፍጻሜ ፡ ወማኅለቅት ። እስመ ፡ እልቦ ፡ ዘይከብር ፡ እምፍኖተ ፡ ምሒር ፡ ወእሠንዮ ፡ ወጸዊረ ፡ ትዕግሥት ።

እሜሃ ፡ ሶበ ፡ ሰምዑ ፡ ተሠጥዎተ ፡ ቃሉ ፡ ለቈስጠንጢኖስ ፡ ፫፻፲፰ቱ ፡ ወጀቱ ፡ ሊቃናት ፡ ጸለዩ ፡ ጸሎተ ፡ ኀበ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ እግዚኦ ፡ አልቦ ፡ ጥንት ፡ ለቅድምናከ ፡ ወለድኅርናከ ፡ አልቦ ፡ ፍጻሜ ፡ እስመ ፡ አንተ ፡ ልዑል ፡ እምነ ፡ መልዕልት ፡ ወአልቦ ፡ መሠረት ፡ ለዕመቅከ ፡ ወአልቦ ፡ ኑኀ ፡ ወግድም ፡ ለመለኮትከ ፤ መንግሥትከኒ ፡ መንግ

የሰማዕታት ፡ ዘመን ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ሃይማኖታቸው ፡ የቀና ፡ ፫፻፲፰ቱ ፡ ሊቃውንት ፡ ቆስጠንጢኖስን ፡ ንጉሥ ፡ ባደረጉት ፡ ጊዜ ፡ እርሱ ፡ እኔ ፡ መንግሥትን ፡ አልሻም ፡ አላቸው ። የክርስቶስ ፡ መንገድና ፡ የዓለም ፡ መንገድ ፡ ልዩ ፡ ነውና ። የክርስቶስ ፡ መንገድና ፡ የተረጋገጠች ፡ ትእዛዙ ፡ ግን ፡ ጠላቶቻችሁን ፡ ውደዱ ፡ ለሚቀሙዋችሁም ፡ በጎ ፡ አድርጉ ፤ (ማቴ ፡ ፭ ፡ ፵፩-፵፬ ። ሉቃ ፡ ፮ ፡ ፳፯-፴፮ ።) ይህንና ፡ የሚመስለውን ፡ ትላለችና ። ይህች ፡ ትእዛዝ ፡ የትሩፋት ፡ ሕግ ፡ ናትና ። ሁለተኛም ፡ እንዲታገሡ ፡ እንዲሸከሙ ፡ ይቅር ፡ እንዲሉ ፡ እንዲያቃልሉ ፡ ለባልንጀሮቻቸውም ፡ ልጆች ፡ መልካም ፡ እንዲያደርጉ ፡ ከሰውነታቸውም ፡ ጋር ፡ እንዲያስተካክሏቸው ፡ (ሉቃ ፡ ፲ ፡ ፲፩ ።) ታዝዛለች ። ይህን ፡ ትእዛዝ ፡ እተው ፡ ዘንድ ፡ ፍርድንና ፡ ያለ ፡ ምሕረት ፡ በጊዜው ፡ ዕዳ ፡ መክፈልን ፡ እዝዝ ፡ ዘንድ ፡ ለተበደለውም ፡ ከበዳዩ ፡ መበቀልን ፡ እዝዝ ፡ ዘንድ ፡ እንዴት ፡ ይቻለኛል ። በሥራ ፡ ፍጹም ፡ የሆነው ፡ ሁሉ ፡ ጉደሎውን ፡ ሊሽረው ፡ ይገባልና ። ስለዚህም ፡ የጌታችን ፡ ሕግ ፡ ከእርስዋ ፡ የሚቀድመውን ፡ ሻረችው ። እርስዋ ፡ ግን ፡ መሻር ፡ አይገባትም ። ከእርስዋ ፡ የሚበልጥ ፡ የለምና ፡ እሷ ፡ የፍጹምነትና ፡ የመጨረሻ ፡ ሕግ ፡ ናት ፡ ከርኅርኄና ፡ መልካም ፡ ከማድረግ ፡ ትዕግሥትንም ፡ ከመያዝ ፡ የበለጠ ፡ ሕግ ፡ የለምና ።

በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የቈስጠንጢኖስን ፡ የቃሉን ፡ መልስ ፡ ሰምተው ፡ ፫፻፲፰ቱ ፡ ሊቃውንት ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ ወደ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንዲህ ፡ እያሉ ፡ ጸሎትን ፡ ጸለዩ ። "አቤቱ ፡ ለቀዳሚነትህ ፡ ጥንት ፡ ለኋለኛነትህም ፡ ፍጻሜ ፡ የለውም ፡ አንተ ፡ ከከፍተኞች ፡ በላይ ፡ ከፍተኛ ፡ ነህና ፡ ለጥልቅነትህ ፡ መሠረት ፡ የለውምና ፡ ለግዛትህም ፡ ወርድ ፡ ቁመት ፡ የለውምና ።

መቅድም

ሐዋርያት ፡ በ፴ትእዛዝ ፡ እምቀኖናት ፡ ዘኍልቆሙ ፡ ፳ወ፭ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘአሕጸጽነ ፡ ንሕነ ፡ ምንተኒ ፡ እምነ ፡ ግብር ፡ ፍትሑ ፡ አንትሙ ፡ በዘይደሉ ፡ እበመ ፡ ብነ ፡ ለኵልነ ፡ መንፈሰ ፡ እግዚአብሔር ። ወብሂሎቶሙኒ ፡ በውስተ ፡ ቀኖናት ፡ ዘ፴ወ፩ ፡ ትእዛዝ ፡ እምኔሃ ፡ ወለእመ ፡ ተርፈ ፡ እምኔነ ፡ ምንትኒ ፡ ያዘክር ፡ ኤጲስቆጶስ ። ወዓዲ ፡ ሀሎ ፡ በውበተ ፡ ቀኖና ፡ ዘ፴ወ፪ ፡ እምኔሃ ፡ ወለእመ ፡ ተርፈ ፡ እምኔነ ፡ ምንትኒ ፡ አፍቁራን ፡ ለዝንቱኒ ፡ ይከሥቶ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዘኮነ ፡ ድልወ ፡ ወትትመራሕ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዘይደሉ ፡ ኀበ ፡ መርሶ ፡ ወዛኅን ።

ወዓዲ ፡ ይቤሉ ፡ ለኤጲስቆጶሳት ፡ በዲድስቅልያ ፡ ፲ቱ ፡ እስመ ፡ ለክሙኒ ፡ ይቤለክሙ ፡ እግዚእነ ፡ "ዘአሰርክሙ ፡ በምድር ፡ ይኩን ፡ እሱረ ፡ በሰማያት ፡ ወዘፈታሕክሙ ፡ በምድር ፡ ይኩን ፡ ፍቱሐ ፡ በሰማያት" ። ወፍትሑ ፡ በሥልጣን ፡ ከመ ፡ እምላክ ።

ወለእመኒ ፡ ፈትሑ ፡ በእንተ ፡ ንስሓሆሙ ፡ ለኃጥአን ፡ በአዝማን ፡ ነዋኅ ፡ አበውሑ ፡ ለሊቃውንት ፡ እቅልሎታ ፡ ወአጽንዖታ ፡ በእምጣነ ፡ ይሬእይዎ ፡ ለተውላጠ ፡ ግብሮሙ ። ወጥንትስ ፡ ዘይገብሩ ፡ ቦቱ ፡ በዝንቱ ፡ ፍካሬ ፡ ኵለንታሁ ፡ ቃለ ፡ እግዚእነ ፡ ውእቱ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ዘይቤሎሙ ፡ ለአርዳኢሁ ፡ "ሑሩ ፡ ወመሀሩ ፡ ኵሎ ፡ አሕዛበ ፡ ወአጥምቅዎሙ ፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወመሀርዎሙ ፡ ይዕቀቡ ፡ ኵሎ ዘአዘዝኩክሙ ፡ ወአነ ፡ እሄሉ ፡ ምስሌክሙ ፡ እስከ ፡ ኅልቀተ ፡ ዓለም" ። ወጥዩቅ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ አሙንቱ ፡ ኢይሄልዉ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፡ ወዕዉቅ ፡ እንከ ፡ ከመ ፡ ለሊሁ ፡ አመረ ፡ በዝንቱ ፡ ቃል ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ይመጽኡ ፡ ድኅሬሆሙ ፡ ወይሠየሙ ፡ ለምሀሮ ፡ ሀየንቴሆሙ ። ወያስተጸንዕ ፡ ዘንተ ፡ በብሂሎቱ ፡ ሎሙ ፡ ወዘእብሎ ፡ ለክሙ ፡ እብል ፡ ለኵሉ ። ወበአንተ ፡ ዝንቱ ፡ ኮነት ፡ ውክፍተ ፡ ቀኖና ፡ ማኅበር ፡ ቅድስት ፡ ወሊቃውንት ፡ ቅዱሳን ፡ ማእምራን ፡ ዘከመ ፡ አቡሊድስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘሮሜ ፡ ወባስልዮስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘቂሳርያ ፡ ወእለ ፡ ይመስልዎሙ ፡ እምሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእለ ፡ እስክንድርያ ።

መሶበሰ ፡ ክነ ፡ ፈቂድ ፡ ኀበ ፡ ሰቢክ ፡ ወፈንዎተ ፡ ሐዋርያት ፡ ውእቱ ፡ አስተሐምሞ ፡ በብከት ፡ ባሕቲቱ ። በከመ ፡ ይቤ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ። ወስብከትሰ ፡ ሕጹር ፡ በእንተ ፡ ሃይማኖት ፡ ወትእዛዘ ፡ ሕይወትሰ ፡ ትሄሉ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ። ኀደጉ ፡ ሰባክያን ፡ ፈሊጠ ፡ ምግባራት ፡

መቅድም

ቍጥራቸው ፡ ፳፭ ፡ ከሆኑት ፡ ቀኖናት ፡ ውስጥ ፡ በ፴ኛው ትእዛዝ ፡ እንዲህ ፡ እንዳሉ ፡ እኛ ፡ ከሥራ ፡ ማናቸውንም ፡ የአጐደልነ ፡ ብንሆን ፡ እናንተ ፡ በሚገባ ፡ አሟሉት ። ለሁላችንም ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ አለንና ። በቀኖናት ፡ ውስጥ ፡ በ፴፩ኛው ፡ ትእዛዝ ፡ ከእኛ ፡ የቀረ ፡ አንዳች ፡ ነገር ፡ ቢኖር ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ ያሳስብ ፡ ማለታቸውም ፡ ይህንኑ ፡ ያስረዳል ። ዳግመኛም ፡ በቀኖናው ፡ ውስጥ ፡ በ፴፪ኛው ፡ ላይ ፡ ወንድሞች ፡ ሆይ ፡ ከእኛ ፡ የቀረ ፡ ምንም ፡ ቢኖር ፡ እግዚአብሔር ፡ ለተገባው ፡ ሰው ፡ ይግለጠው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ጸጥታ ፡ ወዳለው ፡ ወደብ ፡ ትመራ ፡ የሚል ፡ አለ ።

ዳግመኛም ፡ ለኤጲስቆጶሳት ፡ በዲድስቅልያ ፡ በ፲ ኛው ፡ ክፍል ፡ እናንተንም ፡ እኮ ፡ ጌታችን ፡ በምድር ፡ ያሠራችሁት ፡ በሰማይ ፡ የታሠረ ፡ ይሁን ፡ በምድር ፡ የፈታችሁትም ፡ በሰማይ ፡ የተፈታ ፡ ይሁን ፡ እንደ ፡ እምላክም ፡ በሥልጣን ፡ ፍረዱ ፡ ብሏችኋል ፡ አሉ ። (ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፲፰) ።

ስለ ፡ ኃጥአን ፡ በንስሐ ፡ መመለስ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ቢፈርዱ ፡ የሥራቸውን ፡ ለውጥ ፡ በሚያዩዋት ፡ መጠን ፡ ማጽናናትንና ፡ ማቅለልን ፡ ለሊቃውንት ፡ ፈቅደዋል ። ይህን ፡ ትርጓሜ ፡ የሚያደርጉበትም ፡ ጥንተ ፡ ነገር ፡ ምስጋና ፡ ይግባውና ፡ ሁለንተናው ፡ የጌታችን ፡ ቃል ፡ ነው ። ሂዱ ፡ አሕዛብን ፡ ሁሉ ፡ አስተምሩ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ አጥምቋቸው ፡ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ ፡ እንዲጠብቁ ፡ አስተምሩአቸው ፡ እኔም ፡ እስከ ፡ ዓለም ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ እኖራለሁ ፡ ያላቸው ፡ ቃል ፡ ነው ። (ማቴ ፡ ፳፰ ፡ ፲፱-፳) ። እነርሱ ፡ እስከ ፡ ዓለም ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ እንዳይኖሩ ፡ የተረዳ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ቃል ፡ ከእነርሱ ፡ በኋላ ፡ ስለሚመጡትና ፡ በማስተማርም ፡ በእነርሱ ፡ ፈንታ ፡ በለሚሾሙት ፡ የተናገረ ፡ መሆኑን ፡ እርሱ ፡ እንዳስረዳ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ለእናንተ ፡ የምለውን ፡ ለሁሉ ፡ እላለሁ ፡ (ማር ፡ ፲፫ ፡ ፴፯) በማለቱ ፡ ይህን ፡ ያጸናል ። ስለዚህም ፡ የተቀደሰችው ፡ ማኅበርና ፡ ቅዱሳን ፡ ማእምራን ፡ የሆኑ ፡ የሊቃውንቱ ፡ ቀኖና ፡ ተቀባይነትን ፡ ያገኘች ፡ ሆነች ። እኒሁም ፡ እንደ ፡ ሮሜ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ እንደ ፡ አቡሊዲስና ፡ እንደ ፡ ቂሳርያው ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እንደ ፡ ባስልዮስ ፡ ከእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳትም ፡ እነርሱን ፡ እንደሚመስሉት ፡ ያሉት ፡ ናቸው ።

ፈቃድ ፡ ወንጌልን ፡ ለመስበክና ፡ ሐዋርያትን ፡ ለመላክ ፡ ከሆነስ ፡ ለስብከት ፡ መትጋት ፡ ብቻ ፡ ነው ። ጳውሎስ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ የሚደረገው ፡ ስብከት ፡ አጭር ፡ ነው ፡ የሕይወት ፡ ትእዛዝ ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ይኖራል ፡ እንዳለ ። (ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፴፱) ፡ ሰባክያን ፡ በየሀገሩ ፡ የፍርድ ፡

ዘሥርዓት ፡ በውስተ ፡ እህጉር ፡ ለሊቃውንት ።

እስመቦ ፡ እለ ፡ ይጼውዑ ፡ ሰብእ ፡ ኅበ ፡ ኅዲገ ፡ ጥሪት ፡ ፍጹመ ፡ ኢሠርዑ ፡ ሎሙ ፡ ቀኖናተ ፡ ፍሉጣተ ፡ በአንተ ፡ ፍትሐ ፡ ልቃሕያት ፡ ወተባትሮታት ፡ ወለአለ ፡ ይስሕቡ ፡ ኅበ ፡ ኅዲገ ፡ እውስቦ ፡ ኢሠርዑ ፡ ሎሙ ፡ ፍትሐ ፡ ዚእሁ ። ወለእለ ፡ ይከልኡ ፡ አፍቅሮተ ፡ ዓለም ፡ ወዘሀሎ ፡ ውስቴቱ ፡ ኢሐገጉ ፡ ሎሙ ፡ ሥርዓተ ፡ ተናግዶ ወረባኅ ።

ወዓዲ ፡ በቀኖሙ ፡ ሠሪዐ ፡ ምግባራት ፡ ሥጋውያት ፡ እለ ፡ በከሡት ፡ አንተ ፡ መፍትው ፡ ይፍትሑ ፡ ባቲ ፡ መኳንንት ፡ ላዕለ ፡ ሰብእ ፡ በዘተነግረ ፡ በሕግ ፡ ቀዳማዊ፡ ፀውእቱ ፡ኦሪት ፤ በከመ ፡ ተሠርዐ ፡ በአንቀጸ ፡ ዚእሁ ። ወበእንተዝ ፡ ይቤ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሐዋርያ ፡ በ፲ወ፪ ፡ ትእዛዝ ፡ እም፸ወ፩ ፤ አእኃው ፡ መጻሕፍት ፡ ይሜህሩክሙ ፡ በእንተ ፡ ዘተርፉ ፡ ትእዛዛት ፡ ወንሕነኒ ፡ ንነግረክሙ ፡ ዘተአዘዝነ ፡ ቦቱ ።

ወረሰዩ ፡ ጸሕቆሙ ፡ ኅበ ፡ ሕገ ፡ ፍጻሜ ፡ ወኅበ ፡ ፈጽሞተ ፡ ገሥፆተ ፡ ምግባራት ፡ ዘውስጥ ፡ መንፈሳዊት፡ ዘይደልዎ ፡ ለለባዊ ፡ ከመ ፡ የአኃዝ ፡ ባቲ ፡ ነፍሶ ፡ ዘኢይደልዎሙ ፡ ለመኳንንት ፡ ይፍትሑ ፡ ባቲ ፡ ዘከመ ፡ ገሥፆተ ፡ ሕሊናት ፡ ወጠባይዓት ፡ ወመጻእያት ፡ ዘውስጥ ፡ ወእኮ ፡ እንተ ፡ ትትገበር ፡ በመለያልይ ፡ ዘከሡት ። እስመ ፡ ለዝንቱ ፡ ተግሣፅ ፡ ደኃራዊ ፡ ይትረከብ ፡ ቦቱ ፡ ፍጻሜ ፡ ሰብእ ፡ ዘተሣረረ ፡ በነፍስ ፡ ወሥጋ ፡ በገቢረ ፡ ምግባራቲሁ ፡ ነፍሳዊት ፡ ወሥጋዊት ፡ እስመ ፡ ነፍስ ፡ ይእቲ ፡ እንተ ፡ ታንሰሐስሖ ፡ ለሥጋ ፡ ወእምከመ ፡ ተገሠፀ ፡ ኣንሰሐሳሒ ፡ ወኮነ ፡ ፍጹመ ፡ ይትጌሠፃ ፡ ምግባራቲሁ ፡ እለ ፡ ይትገበሩ ፡ በዘያንሰሐስሕ ፡ ዘውእቱ ፡ ሥጋ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ንዋየ ፡ መስቴ ፡ ለነፍስ ።

ወናሁ ፡ ተሠርዐ ፡ በተፍጻሜተ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ ዘይደሉ ፡ ለሊቃውንት ፡ ከመ ፡ ይወስኩ ፡ ዲቤሁ ፡ ወያንትጉ ፡ እምኔሁ ፡ ወእልቦ ፡ ዘኢኮነ ፡ ሎሙ ፡ ብዉሐ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ። ወተዘከረ ፡ በመትሎሁ ፡ ውስተ ፡ እሐዱ ፡ ምዕራፍ ፤ ከመ ፡ ይደሉ ፡ ገቢረ ፡ ቀኖናት ፡ ቃለ ፡ ማኅበር ፡ ዘኒቅያ ፡ በብሂሎቶሙ ። ወለእመ ፡ ተዐደወ ፡ ፩ሂ ፡ ዘእቅደምነ ፡ ወብሀልናሁ ፡ እኮ ፡ ኪያነ ፡ ዘይትቃወም ፡ እላ ፡ ይትቃወሞ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ለይሕትት ፡ ዝንቱ ፡ መጻሕፍተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወያስተሐይጽ ፡ መጻሕፍተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፤ አሜሃ ፡ ይሌቡ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አዘዘነ ፡ በዝንቱ ፡ ኵሉ ።

ወይትዐወቅ ፡ እምቀኖናሆሙ ፡ ከመ ፡ ኵሉ ፡ ዘተ



መጽሐፍን ፡ ለይቶ ፡ መጻፍን ፡ ለሊቃውንት ፡ ተዉ ።

ሰውን ፡ ፈጽሞ ፡ ገንዘብን ፡ ወደመተው ፡ የሚጠሩበት ፡ ጊዜ ፡ ነበረና ፡ ስለ ፡ ብድርና ፡ ስለ ፡ ሽርክና ፡ ለሚፈርደው ፡ ፍርድ ፡ የተለዩ ፡ ሕጎችን ፡ አልሠሩላቸውም ። ጋብቻን ፡ ወደመተው ፡ ለሚያስቡትም ፡ ሰዎች ፡ የዚህን ፡ ፍርድ ፡ አልሠሩላቸውም ። ዓለምንና ፡ በውስጡ ፡ ያለውን ፡ መውደድን ፡ ለሚከለክሉትም ፡ የንግድንና ፡ የትርፍን ፡ ፍርድ ፡ አልደነገጉላቸውም ።

ዳግመኛም ፡ ዳኞች ፡ በሰዎች ፡ ላይ ፡ የሚፈርዱት ፡ ሥጋዊ ፡ ፍርድ ፡ በቀድሞ ፡ ሕግ ፡ በኦሪት ፡ በተነገረውና ፡ በአንቀጹ ፡ በተወሰነው ፡ ይበቃል ፡ ብለው ፡ ለተገለጡት ፡ ሥራዎች ፡ ሕግ ፡ መሥራትን ፡ ተዉ ። ስለዚህም ፡ ሐዋርያው ፡ ጴጥሮስ ፡ ከ፸፩ዱ ፡ ውስጥ ፡ በ፲፪ኛው ፡ ትእዛዝ ፡ "ወንድሞች ፡ ሆይ ፡ ከእኛ ፡ የቀረውን ፡ መጻሕፍት ፡ ያስተምሩአችኋል ፤ እኛም ፡ የታዘዝነውን ፡ እንነግራችኋለን" ፡ አለ ።

ትጋታቸውን ፡ ወደ ፡ ፍጹምነት ፡ ሕግ ፡ ወደ ፡ ወንጌልና ፡ ነፍስ ፡ በሕዋሳት ፡ ውስጥ ፡ የምትሠራቸውን ፡ ሥራዎች ፡ ወደ ፡ መገሠጽ ፡ አደረጉ ። ዐዋቂ ፡ ሰው ፡ መኳንንት ፡ ሊፈርዱባት ፡ የማይቻላቸውን ፡ ነፍሱን ፡ ወስኖ ፡ ለመያዝ ፡ የሚበቃበትን ፡ ይኸውም ፡ በሕዋሳተ ፡ እፍአ ፡ የሚሠሩ ፡ ሥራዎችን ፡ ያይደለ ፡ በሕዋሳተ ፡ ውስጥ ፡ የሚሠሩ ፡ ሥራዎችን ፡ ወስኖ ፡ መያዝ ፡ ነው ። በዚህ ፡ በኋለኛው ፡ ተግሣጽ ፡ ነፍሳዊና ፡ ሥጋዊ ፡ ሥራዎችን ፡ በመሥራት ፡ ከሥጋና ፡ ከነፍስ ፡ የተሠራው ፡ የሰው ፡ ፍጹምነት ፡ ይገኝበታልና ። ሥጋን ፡ የምታንቀሳቅሰው ፡ ነፍስ ፡ ናትና ፤ አንቀሳቃሹ ፡ (ነፍስ) ፡ ከተገሠጸ ፡ ፍጹምም ፡ ከሆነ ፡ በሚንቀሳቀሰው ፡ የሚሠሩት ፡ ሥራዎች ፡ ይገሠጻሉ ፤ ይኸውም ፡ ሥጋ ፡ ነው ። እርሱ ፡ (ሥጋ) ፡ ለነፍስ ፡ እንደ ፡ መሆን ፡ ነውና ።

እነሆ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ለሊቃውንት ፡ የሚገባው ፡ ነገር ፡ ተጽፎአል ፤ በእርሱ ፡ ላይ ፡ እንዲጨምሩ ፡ ከእርሱም ፡ እንዲቀንሱ ፡ በዚህ ፡ ውስጥ ፡ ያልተፈቀደላቸው ፡ ነገር ፡ የለም ። በሚቀጥለው ፡ በምዕራፍ ፡ ፩ ፡ ውስጥም ፡ ቀኖናትን ፡ ማድረግ ፡ እንዲገባ ፡ ተነገረ ። የኒቅያ ፡ ማኅበር ፡ እንዲህ ፡ አሉ ። አስቀድመን ፡ የተናገርነውን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንኳ ፡ ቢያፈርስ ፡ እኛን ፡ የሚቃወም ፡ አይደለም ፤ እርሱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይቃወመዋል ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መጻሕፍት ፡ ይመርምር ፤ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መጻሕፍትንም ፡ ይመልከት ። ያንጊዜ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘን ፡ ይረዳል ።" አሉ ።

አምላክ ፡ በአጻፋቸው ፡ መጻሕፍትና ፡ ሐዋርያት ፡

ንግረ ፡ ባቲ ፡ ኢኮነ ፡ ፍጹመ ፡ ወከመ ፡ ወዘይትዐወቅ ፡ ውስተ ፡ መጻሕፍት ፡ አምላካውያት ፡ ወቀኖናት ፡ ሐዋርያውያት ። ወእመ ፡ እኮስ ፡ እምኑ ፡ ዘተነግረ በቀኖና ሆሙ ፡ ለማኅበር ፡ ደኂሞተ ፡ ነገር ፡ ዘኢይትፈቀድ ፡ ውእቱ ። ወባሕቱ ፡ ተነግረ ፡ እምቀዲሙ ፡ ድሙረ ፡ ዘእን በሰ ፡ ፍልጠት ፡ ወፈለጥዎ ፡ ድኅረ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ዘይትኤነዝ ፡ ወይትሜጠን ፡ በከመ ፡ እቅደምነ ፡ ነጊረ ። ወዝ ንቱ ፡ ውእቱ ፡ ግብሩ ፡ ለዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ ወእምሳሊሁ እምውስተ ፡ ዘተደንገረ ፡ በዘመን ፡ ቦ ፡ ዘይመስል ፡ ለንበ ፡ ዘቀደሞ ፡ ወንስእል ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምሕረተ ፡ ወተሰናስዎ ፡ ወረድኤተ ።

እእምር ፡ ከመ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ ይነግር ፡ መቅ ድመ ፡ ወክልኤተ ፡ ኅብረታተ ፡ ወመቅድምሂ ፡ ይዜኑ ፡ በእንተ ፡ ክልኤቱ ፡ ክፍላት ። ቀዳማዊሰ ፡ ነዋ ፡ ቀደመ ። ዳግማዊኒ ፡ ሀሎ ፡ በዘክሮተ ፡ መጻሕፍት ፡ ወቀኖናት ፡ ዘእስተጋብአ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ ወከሢተ ፡ ትእምርታቲሆሙ ። ለመጻሕፍትሰ ፡ እምላካውያት ፡ ትእምርተ ፡ ፊደሉ ፡ ወንጌል ፡ ፱ ፡ ወለግብረ ፡ ሐዋርያት ፡ ወሐዋ ርያ ፡ ትእምርቶሙ ፡ ስመ ፡ እንባርያን ፡ ቃል ። ወስመል እክታተ ፡ ጳውሎስኒ ፡ ትእምርቶሙ ፡ በስመ ፡ አህጉር ፡ ወበስመ ፡ ብእሲ ፡ ዘጸሐፈ ፡ ሎቱ ፡ መልእክተ ፡ እው ፡ በስመ ፡ ካልእ ፡ እምአስማት ። ለዕብራውያን ፡ ዕብ ፡ ወለጢሞቴዎስ ፡ ጢት ። ወለመጻሕፍተ ፡ አሪትኒ ፡ በ፬ ፡ ፊደላት ፡ እሙንቱ ፡ ወፊደለ ፡ ትእምርተ ፡ አሪት ፡ ቀዳማዊ ፡ ትእ ፡ ወዳግማዊ ፡ ትቢ ፡ ወሣልስ ፡ ትጋ ፡ ወራብዕ ፡ ትዳ ፡ ወኃምስ ፡ ትሔ ፡ ወሆሂ ፡ ኍልቈ ፡ መጻሕፍት ።

ለመጻሕፍተ ፡ ቀኖናትሰ ፡ ቀዳሚሆሙ ፡ ቀኖና ፡ ዘሠርዕዋ ፡ ሐዋርያት ፡ ወእሙንቱ ፡ እንዘ ፡ ጉቡአን ፡ በጽርሐ ፡ ጽዮን ፡ እምድኅረ ፡ ዕርገት ፡ ወርደተ ፡ መን ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ወእምቅድመ ፡ ይዘረው ፡ በእንተ ፡ ስብከት ። ወጸመዉ ፡ መስካውያን ፡ ወንስጥሮሳውያን ፡ በእንተ ፡ ተርጕሞቱ ፡ እምልሳነ ፡ ጽርእ ፡ ኀበ ፡ ዓረቢ ። ወውእቱ ፡ ሀሎ ፡ ኀበ ፡ ያዕቆባውያን ፡ ወስርያ ውያን ፡ ወውእቱ ፡ ጽሑፍ ። ወኍልቁሰ ፡ በኀበ ፡ መለካ ውያን ፡ ፹ ፡ ቀኖናት ፡ ወትእምርተ ፡ ፊደሉኒ ፡ ዓይን ፡ ውእቱ ።

ወዳግማዊ ፡ ቀኖና ፡ ዘአስተናበርዎ ፡ ካዕበ ፡ ሐዋር ያት ፡ ወፈነውዎ ፡ በእደ ፡ ቀሌምንጦስ ፡ ረድኦ ፡ ጴጥ

በሠሩዋቸው ፡ ቀኖናት ፡ የታወቀውና ፡ በእርስዋ ፡ የተነገ ረው ፡ ሁሉ ፡ የተለየ ፡ የተገለጠ ፡ እንዳልሆነ ፡ ከቀኖና ቸው ፡ የተነገ ፡ ይታወቃል ፡ ይህስ ፡ ባይሆን ፡ ኖሮ ፡ በማ ኅበሩ ፡ ቀኖና ፡ የተነገረው ፡ የማይወደድ ፡ ነገርን ፡ መደገ ገም ፡ በሆነ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ መጀመሪያውኑ ፡ ያለ ፡ መለየት ፡ በአንድነት ፡ ተነገረ ። አስቀድመን ፡ እንደተና ገርን ፡ የሚመጠን ፡ የሚያዝ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ በኋላ ፡ ለዩት ። የዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ሥራውና ፡ ልማዱ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡ ከተነገረው ፡ ውስጥ ፡ የቀደመውን ፡ የሚመስል ፡ አለበት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ይቅርታ ንና ፡ ስምምነትን ፡ እርዳታንም ፡ እንለምናለን ።

ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ መቅድምንና ፡ ሁለቱን ፡ ዓይነ ቶች ፡ (ሥጋዊና ፡ መንፈሳዊ ፡) እንደሚናገር ፡ ዕወቅ ። መቅድሙም ፡ ስለ ፡ ሁለቱ ፡ ክፍሎች ፡ ይናገራል ። መጀመ ሪያው ፡ እነሆ ፡ አስቀድሞ ፡ ተነገረ ። ሁለተኛውም ፡ መጻሕፍትንና ፡ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ የሰበሰባቸውን ፡ ቀኖ ናት ፡ በመጥቀስ ፡ ምልክቶቻቸውንም ፡ በመግለጥ ፡ ተነገረ ።

የአምላክ ፡ መጻሕፍት ፡ ግን ፡ የወንጌል ፡ ፊደል ፡ ምልክት ፡ ፱ ፡ ነው ። የግብረ ፡ ሐዋርያትና ፡ የሐዋርያ ፡ ምልክታቸው ፡ መጽሐፉን ፡ ጽፈው ፡ ያኖሩት ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ ነው ። የጳውሎስ ፡ መልእክታትም ፡ ምልክታ ቸው ፡ በአገሮቹ ፡ ስምና ፡ መልእክቱን ፡ በጻፈለት ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ነው ። ወይም ፡ ከስሞቹ ፡ በሌላ ፡ ስም ፡ ነው ። ከዕብራውያን ፡ ሲጠቅስ ፡ ዕብ ፡ ይላል ። ከጢሞቴ ዎስ ፡ ሲጠቅስ ፡ ጢት ፡ ይላል ። የኦሪት ፡ መጻሕፍትም ፡ ምልክታቸው ፡ በሁለት ፡ ፊደሎች ፡ ተወስኖአል ። የመጀ መሪያው ፡ ኦሪት ፡ ምልክት ፡ ትእ ፡ ነው ። የሁለተኛው ፡ ምልክት ፡ ትቢ ፡ የሶስተኛው ፡ ምልክት ፡ ትጋ ፡ የአራ ተኛው ፡ ምልክት ፡ ትዳ ፡ የአምስተኛው ፡ ምልክት ፡ ትሔ ፡ ይላል ። ሆሄ ፡ የመጻሕፍት ፡ መቁጠሪያ ፡ ነው ።

የቀኖና ፡ መጻሕፍት ፡ መጀመሪያቸው ፡ ሐዋርያት ፡ የሠሩዋት ፡ ናት ። እነርሱ ፡ ከዕርገትና ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ከወረደ ፡ በኋላ ፡ ለስብከት ፡ ከመበተናቸ ውም ፡ አስቀድሞ ፡ በጽርሐ ፡ ጽዮን ፡ ተሰብስበው ፡ ሳሉ ፡ የሠሩዋት ፡ ናት ። ንስጥሮሳውያንና ፡ መለካውያን ፡ ይህን ፡ ከግሪክ ፡ ወደ ፡ ዐረቢኛ ፡ ለመተርጐም ፡ ደከሙ ። እር ሱም ፡ በያዕቆባውያንና ፡ በሶርያውያን ፡ ዘንድ ፡ አሁን ፡ አለ ፡ እርሱም ፡ ተጽፎአል ። በመለካውያን ፡ ዘንድ ፡ ቍጥሩ ፡ ፹ ፡ ቀኖና ፡ ነው ። የፊደሉም ፡ ምልክት ፡ ዓይን ፡ ነው ።

ሁለተኛው ፡ ቀኖና ፡ ሐዋርያት ፡ ዳግመኛ ፡ ያዘጋጁ ትና ፡ የሊቀ ፡ ሐዋርያቱ ፡ የጴጥሮስ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡

ሮስ ፡ ሊቀ ፡ ሐዋርያት ፡ ኀበ ፡ ኵሎሙ ፡ አርድእት ፡ ወኀበ ፡ ኵሎሙ ፡ መሃይምናን ። ወተርጕምዎ ፡ ኀበ ፡ ዓረቢ ፡ መለካውያን ፡ ወንስጥሮሳውያን ፡ ውስተ ፡ አሐቲ ፡ መጽሐፍ ። ወኍላቌሃ ፡ በኀበ ፡ መለካውያን ፡ ፹ወ፫ቱ ። ወከማሁ ፡ ውእቱ ፡ በኀበ ፡ ያዕቆባውያን ፡ ወሶርያውያን ። ወኍልቊስ ፡ በኀበ ፡ ንስጥሮሳውያን ፡ በከመ ፡ ይነግር ፡ መጽሐፈ ፡ ኵሎሙ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘአስተጋብአ ፡ ወልደ ፡ ጠይብ ፡ ንስጥሮሳዊ ፡ ፹ወ፪ቱ ። ወትእምርቱሰ ፡ ፬ ፡ ፊደላት ፡ ፪ቱ ፡ እምስመ ፡ ሐዋርያት ፡ ወሣልስ ፡ እምስመ ፡ ረድእ ፡ ዘተፈነወ ፡ በእዴሁ ። ተብህለ ፡ ከመ ፡ አባ ፡ ሚካኤል ፡ ዘሀገረ ፡ ድምያጥ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ እሎንተ ፡ ሕፁረ ፡ ቀኖናተ ፡ አስተጋብአ ፡ ዘውእቶሙ ፡ ፫ቱ ፡ መጻሕፍት ፡ እምኵሉ ፡ ዘተጽሕፉ ፡ እምኔሆሙ ፡ ለለ ፡ አሐዱ ፡ በበኍልቆሙ ፡ ወኢኮነ ፡ አሐዱ ፡ ዘተከሥተ ፡ እምካልአ ፡ ውእቱ ፡ ባሕቲቱ ፡ ከሠቶሙ ፡ ወራብእኒ ፡ ይመርሕ ፡ ስሙ ፡ ዘከመ ፡ ቀዳማዊ ፡ ውእቱ ፡ ወትእምርቱኒ ፡ ረስጦአ ፡ ዘውእቱ ፡ ቀሌምንጦስ ፡ ቀዳማዊ ።

ወግብጻውያንስ ፡ አውፅኡ ፡ በኍልቈ ፡ አሌፍ ፡ ፩ ፡ ቤት ፡ ፪ ፡ ወከመዝ ፡ እስከ ፡ ፲ ፡ ወበኀበ ፡ ካፍሰ ፡ ፳ ፡ ላሜድ ፡ ፴ ፡ ወከመዝ ፡ እስከ ፡ ተፍጻሜቱ ። ወአውፅኡ ፡ ውእቶሙ ፡ ዘንተ ፡ ኀበ ፪ቱ ፡ መጻሕፍት ፡ እለ ፡ ይነግሩ ፡ ለለ ፡ አሐዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘይበዝኅ ፡ እምዘሀሎ ፡ ውስተ ካልኡ ፡ ወኍልቈ ፡ አሐዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ፸ወ፩ቱ ፡ ቀኖና ፡ ወትአምርቱ ፡ ረስጠብ ፡ ዘውእቱ ፡ ቀሌምንጦስ ፡ ዳግም ። ወኍልቈ ፡ ካልኡኒ ፡ ፶ወ፮ቱ ፡ ወትአምርቱኒ ፡ ረስጠጅ ፡ ዘውእቱ ፡ ቀሌምንጦስ ፡ ሣልስ ።

እሎንቱ ፡ መጻሕፍት ፡ ፫ቲሆን ፡ የኀብራ ፡ በነገር ፡ ወፍሉጣት ፡ አማንቱ ፡ በኍልቈ ፡ አክፋል ፡ ኢይዌስክ ፡ አሐዱ ፡ ላዕለ ፡ ካልኡ ፡ ዘእንበለ ፡ በኀዳጥ ።

ወሣልስ ፡ መጽሐፍ ፡ ዘዕዉቅ ፡ በኀበ ፡ ግብጻውያን ፡ ዲድስቅልያ ፡ ዘውእቱ ፡ ትምህርት ፡ ብሂል ፡ ወይነግር ፡ ከመ ፡ አሙንቱ ፡ ተጋብኡ ፡ በእንተ ፡ አንብሮቱ ፡ ውስተ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ሐዋርያት ፡ ወጳውሎስ ፡ ኅሩይ ፡ ወያዕቆብ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘኢየሩሳሌም ። ወጸሐቀ ፡ በእንተ ፡ አውፅኦቱ ፡ ግብጻውያን ፡ ወአልቦ ፡ ውስቴቱ ፡ ምንትኒ ፡ ዘየሐጽጽ ፡ እምቀኖናት ። ወመብዝኅቶ ፡ ረሰዩ ፡ ስምዐ ፡ ውስቴቱ ፡ በውስተ ፡ መካናት ፡ እምወንጌል ፡ ወእምብሉይ ፡ ወኍላቌሁ ፡ ፴ወ፫ቱ ፡ አን



በሆነ ፡ በቀሌምንጦስ ፡ እጅ ፡ ወደ ፡ ምእመናን ፡ ሁሉ ፡ የላኩት ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ። መለካውያንና ፡ ንስጥሮሳውያን ፡ አንድ ፡ መጽሐፍ ፡ አድርገው ፡ ወደ ዐረብኛ ተረጐሙት ። ቊጥሩም ፡ በመለካውያን ፡ ዘንድ ፡ ፹፫ ፡ ነው ። በያዕቆባውያንና ፡ በሶርያውያንም ፡ ዘንድ ፡ ቊጥሩ ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። በንስጥሮሳውያን ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ ቊጥሩ ፡ ግን ፡ ንስጥሮሳዊ ፡ ወልደ ፡ ጠይብ ፡ የሰበሰበው ፡ የክርስቲያኖች ፡ ሁሉ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ሚናገረው ፡ ፹፪ ፡ ነው ። ምልክቱም ፡ አራት ፡ ፊደላት ፡ ናቸው ። ሁለቱ ፡ ከሐዋርያት ፡ ስም ፡ ሦስተኛውም ፡ በእጁ ፡ ከተላከበት ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ስም ፡ ላይ ፡ የተጠቀሰ ፡ ነው ። የድምያጥ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ሚካኤል ፡ እነዚህን ፡ ቀኖናት ፡ አሳጥሮ ፡ እንደ ፡ ሰበሰባቸው ፡ ተነገረ ። እነርሱም ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በየቊጥራቸው ፡ ከተጻፉት ፡ ወገን ፡ የሆኑ ፡ ሦስት ፡ መጻሕፍት ፡ ናቸው ። አንድ ፡ እንኳ ፡ በሌላ ፡ የተገለጠ ፡ አይደለም ። እርሱ ፡ ብቻ ፡ ገለጣቸው ፡ እንጂ ። አራተኛውም ፡ መጀመሪያ ፡ እንደሆነ ፡ ስሙ ፡ ያስረዳል ። ምልክቱም ፡ ረስጦአ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ የመጀመሪያው ፡ ቀሌምንጦስ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ግብጻውያን ፡ ግን ፡ አሌፍን ፡ ፩ ፡ ቤትን ፡ ፪ ፡ ብለው ፡ ቈጠሩ ፡ በዚህም ፡ ሁኔታ ፡ እስከ ፡ ፲ ፡ ቈጠሩ ። ካፍን ፡ ፳ ፡ ላሜድን ፡ ፴ ፡ እደረጉት ። በዚህ ፡ ዓይነት ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ቈጠሩ ። እያንዳንዱ ፡ ባንዱ ፡ ውስጥ ፡ ካለው ፡ የሚበልጥ ፡ የሚናገሩ ፡ ሁለት ፡ መጻሕፍት ፡ አድርገው ፡ አውጣጡት ። ከእነርሱም ፡ ያንዱ ፡ ቊጥር ፡ ፸፩ ፡ ቀኖና ፡ ነው ። ምልክቱም ፡ ረስጠብ ፡ ይላል ። ይኸውም ፡ ሁለተኛው ፡ ቀሌምንጦስ ፡ ማለት ፡ ነው ። የሁለተኛውም ፡ ቊጥር ፡ ፶፮ ፡ ነው ። ምልክቱም ፡ ረስጠጅ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ሦስተኛው ፡ ቀሌምንጦስ ፡ ማለት ፡ ነው ።

እነዚህም ፡ ሦስቱ ፡ መጻሕፍት ፡ በነገር ፡ ይተባበራሉ ። በአከፋፈል ፡ ቊጥር ፡ ግን ፡ የተለያዩ ፡ ናቸው ። አንዱ ፡ በሁለተኛው ፡ ላይ ፡ ከጥቂት ፡ በቀር ፡ አይጨምርም ።

ሦስተኛውም ፡ መጽሐፍ ፡ በግብፃውያን ፡ ዘንድ ፡ ዲድስቅልያ ፡ በመባል ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ትርጓሜውም ፡ ትምህርት ፡ ማለት ፡ ነው ። እርሱን ፡ ጽፎ ፡ ለማኖር ፡ ፲፪ቱ ፡ ሐዋርያትና ፡ የተመረጠው ፡ ጳውሎስ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ያዕቆብም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ እንደ ተሰበሰቡ ፡ ይናገራል ። ግብጻውያን ፡ እርሱን ፡ ተርጕሞ ፡ ለማውጣት ፡ ተጉ ። ከቀኖናት ፡ ምንም ፡ የሚያንስበት ፡ የለውም ። ከውስጡም ፡ በየአንቀጹ ፡ ላይ ፡ አብዛኛውን ፡ ከወንጌልና ፡ ከብሉይ ፡ ምስክር ፡ አደረጉለት ።

ቀጽ ፡ ወትእምርቱ ፡ ድስቅ ፡ ዝ ፡ ውእቱ ፡ ዲድስቅልያ ።

ወራብዕኒ ፡ መልእክተ ፡ ጴጥሮስ ፡ ኀበ ፡ ቀሌምንጦስ ፡ ወትእምርቱ ፡ ጴጥ ፡ ዝ ፡ ውእቱ ፡ ጴጥሮስ ።

ወሐምስ ፡ ቀኖና ፡ ጉባኤ ፡ ቀዳሚሆሙ ፡ ለጉባኤያት ፡ እለ ፡ ተጋብኡ ፡ እምድኅረ ፡ ሐዋርያት ፡ በሀገረ ፡ ዕንቆራ ፡ ዘእምአህጉረ ፡ ገላትያ ። ወኍልቆሙ ፡ ፲ወ፪ ፡ ኤጴስ ቆጶሳት ፡ ወተጋብኡ ፡ በእንተ ፡ ምክንያት ፡ ዘወድቀ ፡ አመ ፡ ዘመነ ፡ ፋርሃት ፡ በዘዘኢአሁ ፡ ክህደት ፡ ወኍልቁ ፡ በመጽሐፈ ፡ ቅብጥ ፡ ፳ወ፭ ፡ ቀኖና ። ወትእምርታሂ ፡ ሰመ ፡ ዚአሃ ።

ወሳድስ ፡ ቀኖና ፡ ማኅበር ፡ ዳግማዊ ፡ ዘተጋብኡ ፡ በቅርጣግና ። ወውእቱ ፡ ህልው ፡ ኀበ ፡ ቂሳርያ ። ወኍል ቆሙ ፡ ፶ ኤጲስቆጶሳት ። ወሠርዑ ፡ ፲ወ፬ተ ፡ ቀኖናተ ፡ በእንተ ፡ ሰብሳብ ፡ ወካህናት ። ወትእምርቱ ፡ ቀጠግ ፡ ዝውእቱ ፡ ቅርጣግና ።

ወሳብዕ ፡ ቀኖና ፡ ጉባኤ ፡ ሣልስ ፡ ዘግንግራ ። ወኍ ልቆሙ ፡ ፲ወ፫ቱ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ዘተጋብኡ ፡ በእንተ ፡ አውግዞቶሙ ፡ ለእለ ፡ የሐርሙ ፡ በሊዐ ፡ ሥጋ ፡ ወአው ስቦ ። ወሠርዑ ፡ ዘንተ ፡ በእንተዝ ፡ ወዘይመስሎ ፡ ፳ ፡ ቀኖናተ ። ወትእምርቱ ፡ ግንር ፡ ዝውእቱ ፡ ግንግራ ።

ወሳምን ፡ ቀኖና ፡ ጉባኤ ፡ ራብዕ ። ወኍልቆሙ ፡ ፲ወ፫ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ዘተጋብኡ ፡ በአንጾኪያ ፡ በእንተ ፡ ክህደተ ፡ ጳውሎስ ፡ ሳሚሳጢ ፡ ሶበ ፡ ይቤ ፡ እስመ ፡ ክር ስቶስ ፡ ሰብእ ፡ ዕራቁ ። ወመተርዎ ፡ ወሠርዑ ፡ ፳ወ፭ተ ፡ ቀኖናተ ፡ በእንተ ፡ ክህነት ። ወትእምርቱ ፡ ጽክ ፡ ዝው እቱ ፡ አንጾኪያ ።

ወታስዕ ፡ ቀኖና ፡ ጉባኤ ፡ ኃምስ ፡ ወውእቱ ፡ ቀዳሚ ሆሙ ፡ ለጉባኤያት ፡ ዐበይት ፡ ዘተጋብኡ ፡ በኒቅያ ፡ በ፫፻ ፳ወ፭ቱ ፡ ዓመት ፡ እምሥጋዌ ፡ ወበ፲ወ፱ ፡ ዓመተ ፡ መን ግሥቱ ፡ ለቈስጠንጢኖስ ፡ ዘየዐቢ ፡ ቀዳሚሆሙ ፡ ለነገ ሥተ ፡ ክርስቲያን ። ወኍልቆሙ ፡ ፫፻፲ወ፰ቱ ፡ ኤጲስ ቆጳሳት ። ወተብህለ ፡ ከመ ፡ እሉ ፡ ተኀርዩ ፡ እም፳፻ወ ፫፻ወ፵ ፡ ኤጲስቆጳሳት ፡ ዘተጋብኡ ፡ በምክንያተ ፡ ክሕ ደቱ ፡ ለአርዮስ ፡ ሶበ ፡ ይቤ ፡ እስመ ፡ ወልድ ፡ ፍጡር ፡ ውእቱ ፡ ወተዋሥአ ፡ እለእክንድሮስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእለ ፡ እስክንድርያ ፡ ወሞዖ ። ወነብሩ ፡ ምስሌሁ ፡ ማኅ

ቍጥሩም ፡ ፹፫ ፡ አንቀጽ ፡ ነው ። ምልክቱም ፡ ድስቅ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ዲድስቅልያ ፡ ማለት ፡ ነው ።

አራተኛውም ፡ ጴጥሮስ ፡ ወደ ፡ ቀሌምንጦስ ፡ የላ ከው ፡ መልእክት ፡ ነው ። ምልክቱም ፡ ጴጥ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ጴጥሮስ ፡ ማለት ፡ ነው ።

አምስተኛውም ፡ የጉባኤ ፡ ቀኖና ፡ ከሐዋርያት ፡ በኋላ ፡ የገላትያ ፡ አገሮች ፡ ክፍል ፡ በሆነች ፡ በዕንቆራ ፡ ከተማ ፡ የተሰበሰቡት ፡ ሊቃውንት ፡ የጻፉት ፡ የጉባኤ ዎች ፡ ተቀዳሚያቸው ፡ ነው ፡ ቍጥራቸውም ፡ ፲፪ ፡ ኤጲ ስቆጶሳት ፡ ነው ። በልዩ ፡ ልዩ ፡ ክሕደት ፡ ምክንያት ፡ ፍርሃት ፡ በበዛበት ፡ ዘመን ፡ ተሰበሰቡ ። ቍጥርዋ ፡ በግ ብጽ ፡ መጽሐፍ ፡ ፳፭ ፡ ቀኖና ፡ ነው ። ምልክቷም ፡ ስሟ ፡ ነው ።

ስድስተኛውም ፡ በቅርጣግና ፡ የተሰበሰቡት ፡ የ፪ኛው ማኅበር ፡ ቀኖና ፡ ነው ። ይኸውም ፡ በቂሳርያ ፡ የሚገኝ ፡ ከተማ ፡ ነው ። ቍጥራቸውም ፡ ፶ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ነው ። ስለ ፡ ጋብቻና ፡ ስለ ፡ ካህናት ፡ ፲፬ ፡ ቀኖናት ፡ ጻፉ ፡ ምል ክቱም ፡ ቀጠግ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ቅርጣግና ፡ ማለት ፡ ነው ።

ሰባተኛውም ፡ በግንግራ ፡ የተደረገ ፡ የሦስተኛው ፡ ጉባኤ ፡ ቀኖና ፡ ነው ። ቍጥራቸውም ፡ ፲፫ ፡ ኤጲስቆጶ ሳት ፡ ነው ። እነርሱም ፡ ሥጋ ፡ መብላትንና ፡ ጋብቻን ፡ የሚከለክሉትን ፡ አውግዞ ፡ ለመለየት ፡ የተሰበሰቡ ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡ ይህንና ፡ የሚመስለውንም ፡ ፳ ፡ ቀኖ ናት ፡ ጻፉ ። ምልክቱም ፡ ግንር ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ግን ግራ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ስምንተኛው ፡ የአራተኛው ፡ ጉባኤ ፡ ቀኖና ፡ ነው ። ቍጥራቸው ፡ ፲፫ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ነው ። እነ ርሱ ፡ በጳውሎስ ፡ ሳሚሳጢ ፡ ክሕደት ፡ ምክንያት ፡ ክርስ ቶስ ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ነው ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ በአንጾኪያ ፡ የተሰበሰቡት ፡ ናቸው ። አውግዘውም ፡ ለዩት ፡ ስለ ፡ ክህነት ፡ ፳፭ ፡ ቀኖናት ፡ ጻፉ ፡ ምልክቱም ፡ ጽክ ፡ ነው ፡ ይኸውም ፡ አንጾኪያ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ዘጠነኛውም ፡ የአምስተኛው ፡ ጉባኤ ፡ ቀኖና ፡ ነው ። እርሱም ፡ የታላላቅ ፡ ጉባኤያት ፡ ተቀዳሚያቸው ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ በ፫፻፳፭ ፡ ዓመት ለክርስቲያን ፡ ነገሥታት ፡ መጀመሪያቸው ፡ የሆነ ፡ ታላቁ ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ በነገሠ ፡ በ፲፱ኛኛው ፡ ዓመት ፡ በኒቅያ ፡ ስብሰባ ፡ የተደረገበት ፡ ነው ። ቍጥራቸው ፡ ፫፻፲፰ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ነው ። እሊህ ፡ ከሁለት ፡ ሺ.ህ ፡ ፫፻፵ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ተመረጡ ፡ ተነገረ ፡ አርዮስ ፡ ወልድ ፡ ፍጡር ፡ ነው ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ በእርሱ ፡ ክሕደት ፡ ምክንያት ፡ የተሰበሰቡ ፡ ናቸው ። የእስክንደ

C ፡ ስመተርቶ ፡ ወስደቱ ፡ ወጸሐፉ ፡ መጽሐፈ ፡ እንተ ፡
ት ፡ ውስቴታ ፡ ሃይማኖት ፡ ርትዕት ። ወሠርዑ ፡
ድኅረ ፡ ፍትሕ ፡ ቀኖናተ ፡ ብዙኃተ ፡ ጥቀ ። ወበዛቲ ፡
ጽሐፍ ፡ ሀለዉ ፡ ፪ቱ ፡ ክፍል ። ለ፩ ፡ እምኔሆሙ ፡
ኍልቁ ፡ ፰ ፡ ቀኖና ፤ ወእምድኅሬሁስ ፡ ቃላት ፡ ብዙ
ኃት ፡ ዘአልቦን ፡ ኍልቈ ። ወውእቱ ፡ ዘይስነዐዉ ፡ ላዕ
ሌሁ ። ወትእምርቱኒ ፡ ኒቅ ፡ ዝ ፡ ውእቱ ፡ ኒቅያ ።

ወካልእኒ ፡ ብዙኅ ፡ ረባኅ ፡ ቦቱ ። ወጸሐቁ ፡ ለአዕል
ምቱ ፡ መለካውያን ፡ ወንስጥሮሳውያን ። ወውእቱ ፡
ንበር ፡ በኀበ ፡ ያዕቆባውያን ፡ ወሶርያውያን ። ወኍ
ልቈ ፡ ዚእሁ ፡ በውስተ ፡ መጽሐፈ ፡ መለካውያን ፡
፹፩ቱ ፡ ቀኖና ። ወዘይተልዋሆን ፡ ቃላት ፡ ዘአልቦን ፡
ኍልቈ ። ወመጽሐፍሰ ፡ ዘሀሎ ፡ ኀበ ፡ መለካውያን ፡
ቱ ፡ ተውሳክ ፡ ለባሕቲቶሙ ፡ ወትእምርቱ ፡ ኒቅያ ።

ዓሥርኒ ፡ ቀኖና ፡ ጉባኤ ፡ ሳድስ ፡ ዘሎዶቅያ ፡ ወኍ
ልቆሙ ፡ ፲ወ፱ ፡ ኤጲስቆጳሳት ፡ ዘተጋብኡ ፡ በእንተ ፡
ማኒ ፡ ወዘይመስልዎ ፡ እምስብእ ፡ ፈጠራ ፡ ዕልዋነ ፡ ሃይ
ማኖት ። ወሠርዑ ፡ ፶ወ፱ተ ፡ ቀኖና ፡ በእንተ ፡ ክህነት ፡
ተዐምዶ ፡ ወአውስቦ ፡ ወዘይመስሎ ። ወይእቲ ፡ ብዝ
ኀተ ፡ ረባኅ ። ወትእምርታ ፡ ዶቅ ፡ ዝ ፡ ውእቱ ፡ ሎዶቅያ።

፲ወ፩ዱ ፡ ቀኖና ፡ ዘጉባኤ ፡ ሳብዕ ፡ ወኍልቆሙ ፡
፪ ፡ ኤጲስቆጳሳት ፡ ዘተጋብኡ ፡ በሰርድቅያ ፡ ፩ ፡ ዘሀ
ገረ ፡ ሮም ፡ ወፍልሰጢን ፡ በእንተ ፡ አርዮሳውያን ፡ እለ ፡
ተንሥኡ ፡ ላዕለ ፡ አትናቴዎስ ፤ ዘውእቱ ፡ ዓሥር ፡ ወታ
ስዑ ፡ እምሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእለ ፡ እስክንድርያ ፡ ወላዕለ ፡
ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእንጾኪያ ፤ ወላዕለ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘቍ
ስጥንጥንያ ። ወሰደድዎሙ ፡ ወሜጥዎሙ ፡ እሉ ፡ ኀበ ፡
ናብርቲሆሙ ፤ ወሠርዑ ፡ ፳ወ፩ደ ፡ ቀኖና ፡ በእንተ ፡
ዓርግ ፡ ኤጲስቆጶሳት ። ወትእምርቱ ፡ ስድቅ ፡ ዝው
እቱ ፡ ሰርድቅያ ።

፲ወ፪ቱ ፡ ቀኖናተ ፡ አቡሊድስ ፡ ሊቀጳጳሳት ፡ ዘሮሜ
ወኍልቆሙ ፡ ፴ወ፰ ፡ ቀኖና ። ወጸሐቁ ፡ በእንተ ፡ አዕ
ልምቱ ፡ ግብጻውያን ። ወውእቱ ፡ ይጼኑ ፡ ረባኅ ፡ ፈድፋደ
ፍሁ ፡ ጸሐፈ ፡ እምኔሁ ፡ አባ ፡ ገብርኤል ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት
ለ ፡ እለክንድርያ ፡ በውስተ ፡ ቀኖና ፡ ዘአስተጋብአ ፡
ኪያሁ ። ወትእምርተ ፡ ስሙ ፡ በደስ ፡ ዝ ፡ ውእቱ ፡ አቡሊ
ድስ ።

ርያው ፡ ሊቀ/፡ ጳጳሳት ፡ እለ ፡ እስክንድሮስ ፡ ተከራክሮ ፡
ረታው ፡ እርሱን ፡ በማውገዝና ፡ በመለየት ፡ ማኅበር ፡
ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ተባበሩ ። የቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ ያለችበት
ንም ፡ መጽሐፍ ፡ ጻፉ ። ከፍርድ ፡ በኋላም ፡ እጅግ ፡ የበዙ፡
ቀኖናትን ፡ ጻፉ ። በዚህች ፡ መጽሐፍም ፡ ሁለት ፡ ክፍሎች ፡
አሉ ። ከነርሱ ፡ የአንዱ ፡ ቍጥር ፡ ፰ ፡ ቀኖና ፡ ነው ። ከእ
ርሱ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ስፍር ፡ ቍጥር ፡ የሌላቸው ፡ ብዙ ፡ ቃላ
ቶች ፡ አሉ ። እነሱም ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ የሚስማሙ ፡
ናቸው ። ምልክቱም ፡ ኒቅ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ኒቅያ ፡
ማለት ፡ ነው ።

ሁለተኛውም ፡ ብዙ ፡ ጥቅም ፡ አለበት ። መለካው
ያንና ፡ ንስጥሮሳውያን ፡ እርሱን ፡ ለመተርጐም ፡ ተጉ ።
እርሱም ፡ በያዕቆባውያንና ፡ በሶርያውያን ፡ ዘንድ ፡ ይገ
ኛል ። ቍጥሩም ፡ በመለካውያን ፡ መጽሐፍ ፡ ፹፩ ፡ ቀኖና
ነው ። የሚከተሏቸውም ፡ ቃሳት ፡ ቍጥር ፡ የላቸውም ።
በመለካውያን ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ ለብ
ቻው ፡ ትርፍ ፡ አለው ። ምልክቱም ፡ ኒቅያ ፡ ነው ።

አሥረኛውም ፡ በሎዶቅያ ፡ የተደረገው ፡ የስድስ
ተኛው ፡ ጉባኤ ፡ ቀኖና ፡ ነው ። ስለማኒና ፡ ሃይማኖትን ፡
ከለወጡ ፡ የልብ ፡ ወለድ ፡ ሰዎች ፡ ወገን ፡ ስለ ፡ ሚመስ
ሉት ፡ የተሰበሰቡት ፡ ኤጲስቆጳሳት ፡ ቍጥራቸው ፡ ፲፱ ፡
ነው ። ስለ ፡ ክህነት ፡ ስለ ፡ አገልግሎት ፡ ስለ ፡ ጋብቻና ፡
ስለሚመስለውም ፡ ፶፱ ፡ ቀኖና ፡ ጻፉ ፡ ይህችውም ፡ ብዙ ፡
ጥቅም ፡ አለባት ። ምልክቷም ፡ ዶቅ ፡ ይላል ። ይኸውም ፡
ሎዶቅያ ፡ ማለት ፡ ነው ።

አሥራ ፡ አንደኛው ፡ የሰባተኛው ፡ ጉባኤ ፡ ቀኖና ፡
ነው ። ቍጥራቸውም ፡ ፪፻ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ነው ። እነ
ርሱም ፡ ከእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ፲፱ኝኛው ፡ በሆ
ነው ፡ በአትናቴዎስና ፡ በአንጾኪያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፤
በቍስጥንጥንያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ላይ ፡ ስለተነሡት ፡
አርዮሳውያን ፡ የፍልስጢንና ፡ የሮም ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡
በሆነች ፡ በሰርድቅያ ፡ የተሰበሰቡ ፡ ናቸው ። እነዚህን ፡
የተነሡትን ፡ አሳረሩዋቸው ። እሊህን ፡ ግን ፡ ወደ ፡ መን
በራቸው ፡ መለሷቸው ። ስለ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ መዓርግ ፡
፳፩ ፡ ቀኖና ፡ ጻፉ ። ምልክቱም ፡ ስድቅ ፡ ይላል ። ይኸ
ውም ፡ ሰርድቅያ ፡ ማለት ፡ ነው ።

አሥራ ፡ ሁለተኛው ፡ የሮሜ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ የአቡ
ሊዲስ ፡ ቀኖና ፡ ነው ። ቍጥራቸውም ፡ ፴፰ ፡ ቀኖና ፡
ነው ። ስለትርጉሙ ፡ ግብጻውያን ፡ ተጉ ። እርሱም ፡
ብዙ ፡ ጥቅም ፡ ይሰጣል ። የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡
አባ ፡ ገብርኤል ፡ እርስዋን ፡ በሰበሰበበት ፡ ቀኖና ፡ ውስጥ
እነሆ ፡ ከእርሱ ፡ ጻፈ ። የስሙም ፡ ምልክት ፡ በደስ ፡
ይላል ። ይኸውም ፡ አቡሊዲስ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፲ወ፫ቱ ፡ ቀኖና ፡ ዘቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ ዐቢይ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘቂሳርያ ፡ በእንተ ፡ ክህናት ፡ ወተሀምዶ ፡ ወአውስቦ ፡ ወዘይመስሎ ፡ ወውእቱ ፡ ቅዉም ፡ በኀበ ፡ ግብጻውያን ፡ ወመለካውያን ፡ ወኍልቁ ፡ ፻ወ፮ቱ ፡ ወሀሎ ፡ ውስቴቱ ፡ ረባኅ ፡ ብዙኅ ፡ ወትእምርቱ ፡ በስ ፡ ዝ ፡ ውእቱ ባስልዮስ ። ወናሁ ፡ ተነግረ ፡ ንስቲት ፡ እምነድላቲሁ ፡ ውስተ ፡ እንቀጸ ፡ መነኮሳት ፡ ወትእምርቱ ፡ በስ ።

፲ወ፬ቱ ፡ ቀኖናት ፡ ዘእሙራት ፡ በቀኖናተ ፡ ነገሥት ፡ ዘውስቴታ ፡ ሥርዓታት ፡ ዓለማውያት ። ወተብህለ ፡ ከመ ፡ ይእቲ ፡ ፬ ፡ መጻሕፍት ፡ ዘአስተጋብእዎሙ ፡ ለነገሥት ፡ እምቃላት ፡ ብዙኃት ፡ በማኅበረ ፡ ኒቅያ ፡ ወተጽሕፈት ፡ በዓውደ ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ ንጉሥ ። ፩ዱ ፡ እምኔሃ ፡ ዘእሙር ፡ በአብጥሊስ ። ወኍልቍሁ ፡ ፵ ፡ አንቀጽ ። ወመለካውያን ፡ አስተጋብእዎ ። ወውእቱ ፡ መጽሐፍ ፡ ሠናይ ፡ ፈድፋደ ። ወትእምርቱ ፡ ጠስ ፡ ዘውእቱ ፡ ተጥላሳት ።

ወለካልእኒ ፡ ኍልቁ ፡ በውስተ ፡ ፪ሆን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ዘግብጽ ፡ ወመለካውያን ፡ ፻ወ፴ ፡ አንቀጽ ወውእቱ ፡ ሀሎ ፡ ኀበ ፡ ንስጡር ። ወናሁ ፡ ጸሐፈ ፡ እምኔሁ ፡ አባ ፡ ገብርኤል ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእለ ፡ እስክንድርያ ፡ በፍጻሜ ፡ መጽሐፉ ። ወትእምርቱ ፡ መክ ፡ ዘውእቱ ፡ ነገሥት ፡ ዳግም ።

ወሣልስ ፡ ዘጽሑቁ ፡ በእስልዎቱ ፡ መለካውያን ። ወኍልቁ ፡ ፳ወ፯ቱ ፡ አንቀጽ ፡ ወትእምርቱ ፡ መጅ ፡ ዝ ፡ ውእቱ ፡ ነገሥት ፡ ሣልስ ፡ ወእሉ ፡ ፪ቱ ፡ መጻሕፍት ፡ እለ ፡ የኀብሩ ፡ እምኔሆሙ ፡ ንስቲት ። ወዘተጽሕፈ ፡ እምኔሁ ፡ ኅዳጥ ፡ ውእቱ ።

ወራብዕኒ ፡ ኍልቁ ፡ ፴ወ፰ቱ ፡ ክፍል ፡ ወቀዳማዊ ፡ እምኔሁ ፡ ተጽሕፈ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ፹ወ፯ ፡ ወካልኡኒ ፡ ፻፹ወ፩ ። ወመብዝኅቱ ፡ እምፍትሐ ፡ አሪት ፡ ወቦ ፡ እምኔሁ ፡ ዘኢየኀብር ፡ ምስለ ፡ ሐዲስ ፡ ሕግ ። ወዘተጽሕፈ ፡ እምኔሁ ፡ ንስቲት ። ወትእምርቱ ፡ መግ ፡ ዘውእቱ ፡ ነገሥት ፡ ራብዕ ። ወዘይበዝኅ ፡ እመጻሕፍተ ፡ ቀኖና ፡ ይትፈለጥ ፡ ኍልቈ ፡ ፩ዱ ፡ ምስለ ፡ ኍልቈ ፡ ካልኡ ፡

ወአልቦ ፡ ካልእ ፡ ዘይነግር ፡ እመጻሕፍት ፡ ወቀኖናት ፡ እንተ ፡ አቅደምነ ፡ ዘክሮቶን ፡ ዘእንበለ ፡ ዜናዊ ፡ ዘውእቱ ፡ ድዮናስዮስ ። ወትእምርቱ ፡ ድ ፡ ወለጎርጎርዮስ ትእምርቱ ፡ ግር ፡ ወለዮሐንስ ፡ አፈወርቅ ፡ ትእምርቱ ፡



አሥራ ፡ ሦስተኛው ፡ የቂሳርያ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ታላቁ ፡ ቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ ስለ ፡ ክህነት ፡ ስለ ፡ ምንኵስና ፡ ስለ ፡ ጋብቻና ፡ ስለ ፡ ሚመስለው ፡ የጻፈው ፡ ቀኖና ፡ ነው ። ይኸውም ፡ በግብጻውያንና ፡ በመለካውያን ፡ ዘንድ ፡ ይገኛል ። ቍጥሩም ፡ ፻፮ ፡ ነው ። በውስጡም ፡ ብዙ ፡ ጥቅም ፡ አለበት ። ምልክቱም ፡ በስ ፡ ይላል ። ይኸውም ፡ ባስልዮስ ፡ ማለት ፡ ነው ።

አሥራ ፡ አራተኛው ፡ በውስጧ ፡ ዓለማውያን ፡ ሥርዓቶች ፡ ያሉባት ፡ በነገሥታት ፡ ሕጎች ፡ የታወቁ ፡ ቀኖናት ፡ ናቸው ። በኒቅያ ፡ ማኅበር ፡ ከብዙዎቹ ፡ ቃላት ፡ ለይተው ፡ ለነገሥታት ፡ የሰበሰቡዋቸውና ፡ በንጉሡ ፡ በቈንጠንጢኖስ ፡ አደባባይ ፡ የተጻፉ ፡ ፬ ፡ መጻሕፍት ፡ እንደሆኑ ፡ ተነገረ ። ከእርስዋ ፡ አንዱ ፡ አብጥሊስ ፡ በመባል ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ቍጥሩም ፡ ፵ ፡ አንቀጽ ፡ ነው ። መለካውያንም ፡ ሰበሰቡት ። ይህም ፡ መጽሐፍ ፡ እጅግ ፡ ጥሩ ፡ ነው ። ምልክቱም ፡ ጠስ ፡ ይላል ። ይኸውም ፡ ተጥላሳት ፡ ማለት ፡ ነው ።

የሁለተኛውም ፡ ቍጥሩ ፡ በግብጽና ፡ በመለካውያን ፡ በሁለቱም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ፻፴ ፡ አንቀጽ ፡ ነው ። እርሱም ፡ በንስጥሮሳውያን ፡ ዘንድ ፡ አለ ። እነሆ ፡ የእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ገብርኤል ፡ በመጽሐፉ ፡ መጨረሻ ፡ ከእርሱ ፡ ጻፈ ። ምልክቱም ፡ መክ ፡ ይላል ። ይኸውም ፡ ሁለተኛው ፡ የነገሥታት ፡ ሕግ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ሦስተኛው ፡ መለካውያን ፡ ለመተርጐም ፡ የደከሙለት ፡ ነው ። ቍጥሩ ፡ ፳፯ ፡ አንቀጽ ፡ ነው ። ምልክቱም ፡ መጅ ፡ ይላል ። ይኸውም ፡ ሦስተኛው ፡ የነገሥታት ፡ ሕግ ፡ ማለት ፡ ነው ። እሊህ ፡ ሁለቱ ፡ መጻሕፍት ፡ የሚተባበሩት ፡ በትንሹ ፡ ነው ። ከእርሱ ፡ የተጻፈውም ፡

አራተኛውም ፡ ቍጥሩ ፡ ፴፰ ፡ ክፍል ፡ ነው ። ከእርሱም ፡ የመጀመሪያው ፡ ፹፯ ፡ አንቀጽ ፡ ሁለተኛውም ፡ ፻፹፩ ፡ አንቀጽ ፡ እንደሆነ ፡ ተጻፈ ። አብዛኛው ፡ ከአሪት ፡ ፍርድ ፡ ነው ። ከእርሱም ፡ ውስጥ ፡ ከሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ ሕግ ፡ ጋር ፡ የማይተባበር ፡ አለበት ። ከእርሱ ፡ የተጻፈውም ፡ ትንሽ ፡ ነው ። ምልክቱም ፡ መግ ፡ ይላል ። ይኸውም ፡ አራተኛው ፡ የነገሥታት ፡ ሕግ ፡ ማለት ፡ ነው ። የሚበዛው ፡ የሕግ ፡ መጻሕፍት ፡ የአንዱ ፡ ቍጥር ፡ ከሁለተኛው ፡ ጋር ፡ ይለያያል ።

አስቀድመን ፡ ከተናገርናቸው ፡ ሕጎችና ፡ መጻሕፍት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የለም ፡ ይኸውም ፡ ሰባኪው ፡ ድዮናስዮስ ፡ ከተናገረው ፡ በቀር ፡ ነው ። ምልክቱም ፡ ድ ፡ ይላል ። የጎርጎርዮስም ፡ ምልክቱ ፡ ግር ፡ ይላል ። የዮሐ

ሐ። ወለክርስቶዶሎስ ፡ ዘውእቱ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስ ፡ እም ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእለ ፡ እስክንድርያ ፡ ትእምርቱ ፡ ክር ስጣ ። ወለጢሞቴዎስ ፡ ትእምርቱ ፡ ጢሞ ።

ወኵሉ ፡ ዘተነግረ ፡ እምቀኖናት ፡ እንዘ ፡ ይፈልጦ ፡ ለካልኡ ፡ ይመውዕዎ ፡ እለ ፡ ይበዝኁ ። ወእለ ፡ ዘልማድ ፡ ዘይደሉ ፡ ለጊዜ ፡ ዘይሰነዐው ፡ ወየኀብር ፡ ምስለ ፡ ልብ ። ዝንቱስ ፡ ቃል ፡ ይከውን ፡ እምቃለ ፡ ፍካሬ ። ወግድፈተ ፡ ቃልስ ፡ ይከውን ፡ እምኢተጠናቅቆ ። ወይደልዎ ፡ ለዘያነብብ ፡ በእዝልፎ ፡ ከመ ፡ ያርትዕ ፡ እምዘተግህደ ፡ በኀቤሁ ።

ተፈጸመ ፡ መቅድም ።



ንስ ፡ አፈወርቅም ፡ ምልክቱ ፡ ሐ ፡ ይላል ። ከእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ወገን ፡ የክርቶዶሎስ ፡ ይኸውም ፡ የክርስቶስ ፡ እገልጋይ ፡ ማለት ፡ ነው ። ምልክቱም ፡ ክርስጣ ፡ ይላል ። የጢሞቴዎስም ፡ ምልክቱ ፡ ጢሞ ፡ ይላል ። ከቀኖናት ፡ ውስጥ ፡ የተነገረው ፡ ሁሉ ፡ ሌላውን ፡ ሲለውጠው ፡ ሲገኝ ፡ የሚበዙት ፡ ያቸንፉታል ። ከጊዜው ጋር ፡ የሚስማሙና ፡ ለልቡና ፡ የሚመጥኑ ፡ የሀገር ፡ ልማዶችም ፡ ያቸንፉታል ። ይኸውም ፡ ቃል ፡ ከትርጓሜ ፡ ቃል ፡ የተገኘው ፡ ነው ። የቃል ፡ ግድፈት ፡ ግን ፡ ካለመጠንቀቅ ፡ የተነሣ ፡ ይሆናል ፡ ዘወትር ፡ ለሚያነብ ፡ ሰው ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ የተገለጠውን ፡ ማቅናት ፡ ይገባዋል ።

መቅድሙ ፡ ተፈጸመ ።

ጕልቈ ፡ አናቅጽ ፡ ዘቀዳማዊ ።

ወኵሉ ፡ ዘቀዳማዊ ፡ ይከውን ፡ ፳ወ፪ቱ ፡ አንቀጽ ፡ በእንተ ፡ ካህናት ፡ ወሕገገ ፡ ቅኔ ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚ አብሔር ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

## ክፍል ቀዳማዊ ።

አንቀጽ ፡ ቀዳማዊ ፡ በእንተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወበእ ንተ ፡ ኵሉ ፡ ዘይደሉ ፡ ላቲ ።

፪ ፡ በእንተ ፡ ጥንተ ፡ መጻሕፍት ፡ ውኩፋት ።

፫ ፡ በእንተ ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ ወእለ ፡ ይበውኡ ፡ ውስተ ፡ ሃይማኖት ።

፬ ፡ በእንተ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ።

፭ ፡ በእንተ ፡ ኤጲስቆጶሳት ።

፮ ፡ በእንተ ፡ ቀሳውስት ።

፯ ፡ በእንተ ፡ ዲያቆናት ።

፰ ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ተርፉ ፡ ላእካነ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን።

፱ ፡ በእንተ ፡ ካህናት ።

፲ ፡ በእንተ ፡ መነኰሳት ፡ ወመነኰሳይያት ።

፲ወ፩ ፡ በእንተ ፡ ተግሣጽ ፡ ወትእዛዘ ፡ ሕዝብ ።

፲ወ፪ ፡ በእንተ ፡ ቅዳሴ ።

፲ወ፫ ፡ በእንተ ፡ ቍርባን ።

፲ወ፬ ፡ በእንተ ፡ ጸሎት ።

፲ወ፭ ፡ በእንተ ፡ ጾም ።

፲ወ፮ ፡ በእንተ ፡ ምጽዋት ።

፲ወ፯ ፡ በእንተ ፡ ዘይሠየም ፡ ለከፊለ ፡ ምጽዋት ።

፲ወ፰ ፡ በእንተ ፡ ዓሥራት ፡ ወበኵራት ፡ ወብጽዓታት ፡ ወጕልታት ።

፲ወ፱ ፡ በእንተ ፡ እሑዳት ፡ ወበዓላት ።

፳ ፡ በእንተ ፡ ሰማዕታት ፡ ወተእማንያን ፡ ወከሀድ ያን ።

፳ወ፩ ፡ በእንተ ፡ ድዉያን ።

፳ወ፪ ፡ በእንተ ፡ ሙታን ።

ተፈጸመ ፡ ክፍል ፡ ቀዳማዊ ።

የመጀመሪያው ፡ አንቀጽ ፡ ቍጥር ።

መጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ ስለ ፡ ካህናትና ፡ ስለ ፡ አገል ግሎት ፡ ሕጎች ፡ የሚናገር ፡ ፳፪ ፡ አንቀጽ ፡ ነው ። ለእግዚ አብሔር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ።

## መጀመሪያ ፡ ክፍል ።

አንቀጽ ፡ ፩ ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለእርሷ ፡ ስለሚ ገባው ፡ ሁሉ ።

አንቀጽ ፡ ፪ ፡ ሊቀበሏቸው ፡ ስለሚገቡ ፡ ጥንታውያን ፡ መጻሕፍት ።

አንቀጽ ፡ ፫ ፡ ስለ ፡ ክርስትና ፡ ጥምቀትና ፡ ወደ ፡ ሃይማ ኖት ፡ ስለሚገቡ ፡ ሰዎች ።

አንቀጽ ፡ ፬ ፡ ስለ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ።

አንቀጽ ፡ ፭ ፡ ስለ ፡ ኤጲስቆጶሳት ።

አንቀጽ ፡ ፮ ፡ ስለ ፡ ቀሳውስት ።

አንቀጽ ፡ ፯ ፡ ስለ ፡ ዲያቆናት ።

አንቀጽ ፡ ፰ ፡ ስለቀሩት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልጋ ዮች ።

አንቀጽ ፡ ፱ ፡ ስለ ፡ ካህናት ፡ ሁሉ ።

አንቀጽ ፡ ፲ ፡ ስለ ፡ መነኰሳትና ፡ ስለ ፡ መነኰሳይያት ።

አንቀጽ ፡ ፲፩ ፡ ስለ ፡ ሕዝብ ፡ ትእዛዝና ፡ ተግሣጽ ።

አንቀጽ ፡ ፲፪ ፡ ስለ ፡ ቅዳሴ ።

አንቀጽ ፡ ፲፫ ፡ ስለ ፡ ቍርባን ።

አንቀጽ ፡ ፲፬ ፡ ስለ ፡ ጸሎት ።

አንቀጽ ፡ ፲፭ ፡ ስለ ፡ ጾም ።

አንቀጽ ፡ ፲፮ ፡ ስለ ፡ ምጽዋት ።

አንቀጽ ፡ ፲፯ ፡ ምጽዋትን ፡ ለማደል ፡ ስለሚሾም ።

አንቀጽ ፡ ፲፰ ፡ ስለ ፡ አሥራትና ፡ ስለ ፡ በኵራት ፡ ስለ ፡ ስእለት ፡ ስለ ፡ ጕልቶች ።

አንቀጽ ፡ ፲፱ ፡ ስለ ፡ እሑዶችና ፡ ስለ ፡ በዓላት ።

አንቀጽ ፡ ፳ ፡ ስለ ፡ ሰማዕታት ፡ ስለ ፡ እማንያንና ፡ ስለ ፡ ከሐድያን ።

አንቀጽ ፡ ፳፩ ፡ ስለ ፡ ድዉያን ።

አንቀጽ ፡ ፳፪ ፡ ስለ ፡ ሙታን ።

መጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ ተፈጸመ ።

## ኊልቈ ፡ አናቅጽ ፡ ዘዳግማዊ ።

ክፍል ፡ ዳግማዊ ፡ በእንተ ፡ ግብራት ፡ ዓላማውያት ፡ ዘምግብና ።

ምግብናሰ ፡ ዘሰብእ ፡ ባሕቲቱ ፡ በሐሳበ ፡ ሰብእና ሁ ፡ ወግእዙ ፡ ውእቱ ፡ ዘከመ ፡ መባልዕት ፡ ወአልባስ ፡ ወአብያት ፡ ወአውስቦ ፡ ወሕርመተ ፡ ዕቁባት ።

ወምግብናሰ ፡ ዘበበሥርዓታ ፡ ናሁ ፡ አቅደምነ ፡ መብዝኅታ ፡ በአንቀጸ ፡ ተግሣፆሙ ፡ ለሕዝባውያን ፡ ከመ ፡ ይንበር ፡ ብእሲ ፡ ምስለ ፡ ብእሲቱ ፡ ወወልዱ ፡ ወገብሩ ። ወምግብናሰ ፡ ሀገራዊት ፡ ዘከመ ፡ ተናግዶ ፡ ወተፋትሖ ፡ ወኵነኔ ፡ ፍትሕ ፡ ዘበእንተ ፡ አበሳት ፡ ውእቱ ፡ ወኊልቆሙ ፡ ፹ወ፱ቱ ፡ አንቀጽ ፡ ለፍጻሜ ፡ ፻ወ፩ዱ ፡ አንቀጽ ።

፹ወ፫ ፡ በእንተ ፡ መባልዕት ፡ ወአልባስ ፡ ወአብያት ፡ ወተግባራት ።

፹ወ፬ ፡ በእንተ ፡ ሕጼ ፡ ወውሂበ ፡ ንዋይ ፡ ዘአቅሞ ፡ ሰብሳብ ፡ ወአውስቦ ።

፹ወ፭ ፡ በእንተ ፡ ሕርመተ ፡ ዕቁባት ።

፹ወ፮ ፡ በእንተ ፡ ሀብት ።

፹ወ፯ ፡ በእንተ ፡ ልቃሕ ፡ ወተሐብዮ ፡ ወአኅዝ ፡ ወአመግቦ ።

፹ወ፰ ፡ በእንተ ፡ ሕስት ፡ ከመ ፡ ልብስ ፡ ወእንስሳ ፡ ወካልኢሆሙ ።

፹ወ፱ ፡ በእንተ ፡ ምዕቅብና ፡ ንዋይ ፡ ወዘይመስሎ ።

፺ ፡ በእንተ ፡ ምግብና ።

፺ወ፩ ፡ በእንተ ፡ ግብርናት ፡ ወግእዛን ፡ ወእግአዚ ፡ ገብር።

፺ወ፪ ፡ በእንተ ፡ ሐፃኒ ፡ ዘከመ ፡ ሕቅፈተ ፡ ሕፃን ፡ በኵሉ ፡ ግብሩ ።

፺ወ፫ ፡ በእንተ ፡ ሤጥ ፡ ወተሣይጦ ፡ ወመትሎሆሙ ።

፺ወ፬ ፡ በእንተ ፡ ተሳትፎ ፡ ንዋይ ፡ ወዘይመስሎ ፡ ለዝንቱ ፡ ግብር ።

፺ወ፭ ፡ በእንተ ፡ አገብሮ ፡ ወመዓት ።

፺ወ፮ ፡ በእንተ ፡ ተዓስቦ ፡ ቤት ፡ ወውሂበ ፡ ንዋይ ፡ ለምድር ፡ ዘከመ ፡ ገመታ ።

፺ወ፯ ፡ በእንተ ፡ ሐኒጸ ፡ ሕንፃ ፡ ወዘይተልዎ ።

፺ወ፰ ፡ በእንተ ፡ ልቃሕ ።

፺ወ፱ ፡ በእንተ ፡ ተአምኖ ፡ ኃጣውእ ።

፻ ፡ በእንተ ፡ ረኪብ ፡ ዘተገድፈ ፡ እምእንስሳ ፡ ወዘይመስሎ ።

## የሁለተኛው ፡ አንቀጽ ፡ ቍጥር ።

ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ዓለማውያን ፡ ስለሆኑ ፡ የአስተዳደር ፡ ሥርዓቶች ።

የአስተዳደር ፡ ሹመት ፡ ግን ፡ እካለ ፡ መጠን ፡ ያደረሰና ፡ ጠባዩ ፡ ያማረ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ መጠን ፡ የሰው ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ እንደ ፡ መብል ፡ እንደ ፡ ልብስ ፡ እንደ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ጋብቻ ፡ ያለውና ፡ ከዕቁባት ፡ እንደ ፡ መከልከል ፡ ያለውን ፡ ነው ። በየሥርዓቷ ፡ የሆነውን ፡ አስተዳደር ፡ ግን ፡ አብዛኛዋን ፡ እነሆ ፡ በሕዝባውያን ፡ ተግሣጽ ፡ አንቀጽ ፡ አስቀደምነ ። ወንድ ፡ ከሚስቱና ፡ ከልጁ ከሎሌውም ፡ ጋር ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ። ሀገራዊት ፡ አስተዳደር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ንግድ ፡ እንደ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ እንደ ፡ ወንጀል ፡ ፍርድ ፡ ያለው ፡ ነው ። ቍጥራቸውም ፡ ፹፱ ፡ አንቀጽ ፡ ነው ። በመጨረሻም ፡ ድምሩ ፡ ፻፩ ፡ አንቀጽ ፡ ነው ።

አንቀጽ ፡ ፹፫ ፡ ስለ ፡ መብል ፡ ስለ ፡ ልብስ ፡ ስለ ፡ ቤትና ፡ ስለ ፡ ተግባረ ፡ እድ ።

አንቀጽ ፡ ፹፬ ፡ ስለ ፡ ማጨት ፡ ጋብቻን ፡ ለማጽናት ፡ ገንዘብ ፡ ስለመስጠትና ፡ ስለ ፡ ጋብቻ ።

አንቀጽ ፡ ፹፭ ፡ ከዕቁባት ፡ ስለ ፡ መከልከል ።

አንቀጽ ፡ ፹፮ ፡ ስለ ፡ ስጦታ ።

አንቀጽ ፡ ፹፯ ፡ ስለ ፡ ብድር ፡ ስለ ፡ ዋስትና ፡ ስለ ፡ መያዣ ለአስተዳዳሪነት ፡ ስለመሾም ።

አንቀጽ ፡ ፹፰ ፡ እንደ ፡ ልብስና ፡ እንደ ፡ እንስሳ ፡ ያሉትንና ፡ ሌሎችንም ፡ ስለ ፡ መዋስ ።

አንቀጽ ፡ ፹፱ ፡ ገንዘብን ፡ በአደራ ፡ ስለማስጠበቅና ፡ ስለሚመስለውም ።

አንቀጽ ፡ ፺ ፡ በአስተዳዳሪነት ፡ ስለመሾም ።

አንቀጽ ፡ ፺፩ ፡ ስለ ፡ ባርነት ፡ ስለ ፡ ነፃነት ፡ ባሪያንም ፡ ነፃ ፡ ስለ ፡ ማውጣት ።

አንቀጽ ፡ ፺፪ ፡ ስለ ፡ ሞግዚት ፡ ሕፃንን ፡ በሥራው ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ መከባከብ ።

አንቀጽ ፡ ፺፫ ፡ ስለ ፡ መሸጥና ፡ ስለመግዛት ፡ እነርሱንም ስለሚከተለው ።

አንቀጽ ፡ ፺፬ ፡ ስለ ፡ ሽርክና ፡ ይህንንም ፡ ሥራ ፡ ስለሚመስለው ።

አንቀጽ ፡ ፺፭ ፡ ስለ ፡ ማስገደድና ፡ ስለቍጣ ።

አንቀጽ ፡ ፺፮ ፡ ቤትን ፡ ስለ ፡ ማከራየት ፡ እንደ ፡ ግምቷ ፡ ስለ ፡ ምድር ፡ ገንዘብን ፡ ስለመስጠት ።

አንቀጽ ፡ ፺፯ ፡ ስለ ፡ ቤት ፡ ሥሩና ፡ ስለሚመስለውም ።

አንቀጽ ፡ ፺፰ ፡ ስለ ፡ ብድር ።

አንቀጽ ፡ ፺፱ ፡ ኃጢአትን ፡ ስለ ፡ ማመን ።

አንቀጽ ፡ ፻ ፡ ከእንስሳው ፡ ወገን ፡ የጠፋውን ፡ ስለማግኘትና ፡ ስለሚመስለውም ።

ጐልቄ ፡ አናቅጽ ፡ ዘዳግማዊ ።

፺ወ፩ ፡ በእንተ ፡ ጽሒፈ ፡ ትእዛዝ ፡ በንዋይ ።

፺ወ፪ ፡ በእንተ ፡ ርስት ።
፺ወ፫ ፡ በእንተ ፡ ፈታሒ ፡ ወዘምስሌሁ ።
፺ወ፬ ፡ በእንተ ፡ ነገሥት ።
፺ወ፭ ፡ በእንተ ፡ ብሉይ ፡ ወሐዲስ ።
፺ወ፮ ፡ በእንተ ፡ ዘነኔ ፡ ከሓድያን ።
፺ወ፯ ፡ በእንተ ፡ ቀታልያን ።
፺ወ፰ ፡ በእንተ ፡ ተግማፀ ፡ ዝሙት ።
፺ወ፱ ፡ በእንተ ፡ ዘነኔ ፡ ሰረቅት ።
፻ ፡ በእንተ ፡ ጐልቄ ፡ ኃጣውእ ።
፻ወ፩ ፡ በእንተ ፡ ዘዘዚአሁ ፡ ጐልቄ ፡ ምግባራት ።

ተፈጸመ ፡ አንቀጽ ፡ ፻ወ፩ዱ ።

የሁለተኛው ፡ አንቀጽ ፡ ቍጥር ።

አንቀጽ ፡ ፺፩ ፡ በገንዘብ ፡ ላይ ፡ ለማዘዝ ፡ ኑዛዜ ፡ ስለ ፡ መጻፍ ።
አንቀጽ ፡ ፺፪ ፡ ስለ ፡ ርስት ።
አንቀጽ ፡ ፺፫ ፡ ስለ ፡ ዳኛና ፡ ስለ ፡ ረዳቶቹ ።
አንቀጽ ፡ ፺፬ ፡ ስለ ፡ ነገሥታት ።
አንቀጽ ፡ ፺፭ ፡ ስለ ፡ ብሉይና ፡ ስለ ፡ ሐዲስ ።
አንቀጽ ፡ ፺፮ ፡ ስለ ፡ ከሀድያን ፡ ቅጣት ።
አንቀጽ ፡ ፺፯ ፡ ስለ ፡ ነፍሰ ፡ ገዳዮች ።
አንቀጽ ፡ ፺፰ ፡ ስለ ፡ ዝሙት ፡ ቅጣት ።
አንቀጽ ፡ ፺፱ ፡ ስለ ፡ ሌቦች ፡ ቅጣት ።
አንቀጽ ፡ ፻ ፡ ስለ ፡ ኃጢአት ፡ ቍጥር ።
አንቀጽ ፡ ፻፩ ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራዎች ፡ ቍጥር ።

የ፻፩ዱ ፡ አንቀጽ ፡ እርእስት ፡ ተፈጸመ ።

በስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዋሕድ ፡ በመለኮት ፡ ዘይሤለስ ፡ በአካላት ፡ ወኩነታት ፡

## አንቀጽ ቀዳማዊ

በእንተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን

ወዘይደሉ ፡ ላቲ ፡፡

፩ ጅ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንሰ ፡ ቤተ ፡ ጸሎት ፡ ይእቲ ፡

፪ በስ ፡ ፺ወ፬ ፡ ወኢይሕንጹ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘእንበለ ፡ በትእዛዘ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወለእመ ፡ ተሀበለ ፡ ፩ዱሂ ፡ ወገብረ ፡ ካልእ ፡ እምዝንቱ ፡ ኢይቅረብ ፡ ቍርባን ፡ በውስቴታ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፡ ወለእመ ፡ ተሀበለ ፡ ካህን ፡ ዘንተ ፡ ወቀረበ በውስቴታ ፡ ቍርባን ፡ ይትመተር ፡፡

፫ ወከዊን ፡ ሕንፃሃ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወሥርዓታ ፡ ሀሎ ፡ በውስተ ፡ ክፍል ፡ ዘ፲ወ፰ቱ ፡ ወበ፴ ፡ እምዲድስቅልያ ፡፡ ወትኩን ፡ ብርሀተ ፡ በብዙኅ ፡ መኃትው ፡ በአምሳለ ፡ ሰማይ ፡ ወፈድፋደስ ፡ ጊዜ ፡ ያነብቡ ፡ ክፍላተ ፡ መጻሕፍት ፡ ቅዱሳት ፡ ዘውእቶሙ ፡ ጳውሎስ ፡ ወሐዋርያ ፡ ወግብር ፡ ወወንጌለ ፡ መንግሥትስ ፡ ትኩን ፡ ብርሀተ ፡ ጥቀ ፡፡

፬ ጼጥ ፡ ወያኀትዉ ፡ በሰምዕ ፡ ወቀንዲል ፡ ጊዜ ፡ ይቄድስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ታቦታተ ፡ ምሥዋዕ ፡ ወየሀልዉ ፡ ምስሌሁ ፡ ጊዜ ፡ ቅዳሴሃ ፡ ፲ቱ ፡ ቀሳውስት ፡ ወይኅትም ፡ ኪያሃ ፡ በሜሮን ፡ ዘውእቱ ፡ ቅብዐ ፡ ትፍሥሕት ፡ እስመ ፡ ማኅተመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይቀድሱ ፡ በውስቴታ ፡፡

፭ ወያንብቡ ፡ ዲበ ፡ምሥዋዕ ፡ ወንጌለ ፡ ዮሐንስ ፡ አምላካዊ ፡ ወኢይቀድሱ ፡ በላዕሌሁ ፡ ቀዳሚ ፡ ዘእንበለ ፡ ይትጋብኡ ፡ ቀሳውስት ፡ ወሊቃኑ ፡ ወዙሎሙ ፡ ዲያቆናት ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ዝንቱ ፡ ክብረ ፡ ወፍሥሓ ፡፡

፮ ወለእመ ፡ ተሰብረ ፡ ምሥዋዕ ፡ አው ፡ ፈለሰ ፡ ይቀድሱ ፡ ዳግመ ፡ ወይኩን ፡ ታቦት ፡ በዘይፈልስ ፡ እመካን ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ ከመ ፡ እብነ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ዘፈለሰ ፡ እመካን ፡ ውስተ ፡

በመለኮት ፡ አንድ ፡ በአካላትና ፡ በሁኔታዎች ፡ ፫ ፡ በሆነ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡፡

## አንቀጽ፡ ፩ ፡፡

ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡

ለእርስዋ ፡ ስለሚገባው ፡፡

፩ ጅ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ግን ፡ የጸሎት ፡ ቤት ፡ ናት ፡፡(ማቴ ፡ ፳፩ ፡ ፲፫ ፡፡ ማር ፡ ፲፩ ፡ ፲፯ ) ፡፡

፪ በስ ፡ ፺፬ ፡፡ ያለ ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ ትእዛዝ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ አይሥሩ ፡፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሰንኳ ፡ ደፍሮ ፡ ከዚህ ፡ ውጪ ፡ ቢሠራ ፡ በውስጥዋ ፡ እስከ ፡ ዘላለም ፡ ቍርባን ፡ አይቅረብ ፡፡ ቄሱም ፡ ይህን ፡ ተላልፎ ፡ በውስጥዋ ፡ ቍርባንን ፡ ቢቈርብ ፡ ይሻር ፡፡

፫ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሠራር ፡ ሁኔታና ፡ ሥርዓትዋ ፡ በዲድስቅልያ ፡ በ፲፰ኛውና ፡ በ፴ኛው ፡ ክፍል ፡ ይገኛል ፡፡ በሰማይ ፡ አምሳል ፡ በብዙ ፡ መብራቶች ፡ የበራች ፡ ትሁን ፡፡ ይልቁንም ፡ የቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ ክፍሎች ፡ በሚያነቡበት ፡ ጊዜ ፡ እነርሱም ፡ ጳውሎስና ፡ ሐዋርያ ፡ የሐዋርያት ፡ ሥራ ፡ ናቸው ፡ ወንጌለ ፡ መንግሥት ፡ በሚያነቡበት ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ በጣም ፡ የበራች ፡ ትሁን ፡፡

፬ ጼጥ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ የመሠውያውን ፡ ታቦት ፡ በሚባርክበት ፡ ጊዜ ፡ በሰምና ፡ በዘይት ፡ ያብሩ ፡፡ በምትባረክበትም ፡ ጊዜ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ሰባት ፡ ቀሳውስት ፡ ይኑሩ ፡፡ የደስታ ፡ ቅባት ፡ በሆነ ፡ በሜሮን ፡ ይቀቡዋት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማኅተም ፡ ነውና ፡፡ በውስጥዋም ፡ ይቀድሱ ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ፡፡

፭ በመሠውያው ፡ (በመንበሩ ፡) ላይ ፡ እምላካዊ ፡ የሆነ ፡ የዮሐንስ ፡ ወንጌልን ፡ ያንብቡ ፡፡ ቀሳውስትና ፡ አለቆቻቸው ፡ ዲያቆናቱም ፡ ሁሉ ፡ ሳይሰበሰቡ ፡ አስቀድመው ፡ በላዩ ፡ አይቀድሱ ፡ ይህ ፡ ደስታና ፡ ክብር ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡፡

፮ መሠውያው ፡ ቢሰበር ፡ ወይም ፡ ቢፈልስ ፡ (ቢማረክ ፡ ) ዳግመኛ ፡ ይቀድሱት ፡ ታቦቱ ፡ ከቦታ ፡ ወደ ፡ ቦታ ፡ ይዛወር ፡ እንደነበረው ፡ እንደ ፡ ቿኤል ፡ ልጆች ፡ ታቦት ፡ ከቦታ ፡ ወደ ፡

መካን ።
፯ በስ ፡ ፶ወ፯ ፡ በደስ ፡ ፳ወ፱ ፡ ወመሬተ ፡ ምሥዋ ዕኒ ፡ ዘይኩስትርዎ ፡ እምኔሁ ፡ ይግድፍዎ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡ ዘይውኅዝ ፡
፰ ረስጣ ፡ ፳ወ፰ ፡ ወኵሉ ፡ ዘኮነ ፡ እምቤተ ፡ ክርስ ቲያን ፡ እምንዋይ ፡ ዘተቀደሰ ፡ እመኒ ፡ ንዋየ ፡ ወርቅ ፡ ወብሩር ፡ ኢይደልዎ ፡ ለብእሲ ፡ ከመ ፡ ይትገበር ፡ ቦሙ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ዐሊወ ፡ ሕግ ፡ ውእቱ ፡ ወለእመ ፡ ገብረ ፡ ዘንተ ፡ ይሰደድ ፡ እምድኅረ ፡ ተኰነነ ፡ እምቤተ ክርስቲያን ።
፱ ረስጣ ፡ ፲ወ፱ ፡ ወዘውፁእን ፡ እምሃይማኖት ፡ ዳግመ ፡ ሰእመ ፡ ጸንዑ ፡ ዲበ ፡ ምእመናን ፡ ወከ ልእዎሙ ፡ እምሐዊር ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይቀድስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ። ወለእ መሰ ፡ ኢተክህለ ፡ ዝንቱ ፡ ከመ ፡ ይትጋብኡ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ውስተ ፡ ፩ዱ ፡ ቤት ፡ እው ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይዘምር ፡ ኵሉ ፡ ለለ፩ዱ ፡ በኀበ ፡ ሀለወ ፡ ውእቱ ፡ ባሕቲቱ ፡ ወያ ንብብ ፡ ወይጸሊ ።
፲ ዶቅ ፡ ፶ወ፫ ፡ ወኢያዕርጉ ፡ ቍርባነ ፡ ውስተ ፡ አብያቲሆሙ ፡ ለኤጲስ-ቆጳሳት ፡ ወኢኀበ ፡ ፩ሂ ፡ እምቤተ ፡ ምእመናን ፡ ዘእንበለ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘተቀደሰት ፡ ግንር ፡ ፯ ፡ ወእመቦ ፡ ዘተዐደወ ፡ ላዕለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ ያን ፡ ወገብረ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡ ግብረ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንተ ፡ ኢትትገበር ፡ ዘእንበለ ፡ በኀቤሃ ፡ ውጉዘ ፡ ለይኩን ።
፲፩ በደስ ፡ ዘ፳ወ፱ ፡ ወኢይንበር ፡ ፩ሂ ፡ ውስተ ፡ መካነ ፡ ምሥዋዕ ፡ ዘእንበለ ፡ ለጸሎት ፡ ባሕ ቲታ ፡ ወሰስጊድ ፡ በቅድመ ፡ ምሥዋዕ ። ዘ፲ ወ፱ ፡ ወኢይደልዎ ፡ ለአሐዱሂ ፡ እምእመናን ፡ ለእመ ፡ ኢኮነ ፡ ካህነ ፡ ከመ ፡ ይባእ ፡ ኀበ ፡ ምሥ ዋዕ ፡ ከመ ፡ ይትመጠው ፡ ቍርባነ ።

፲፪ ዶቅ ፡ ዘ፳ወ፰ ፡ ኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይጸውዑ ፡ ሰረፌቅ ፡ ወለምሳሕ ፡ ውስተ ፡ አብያተ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ወታቦታቲሁ ፡ ቅዱሳት ፡ ቆሮንቶስ ፡ ዘ፲ወ፩ ፡ ወኢታስተሐቅሩ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወኢታስተኀፍርዎሙ ፡ ለእለ ፡ አልቦሙ ፡ ምንትኒ ፡ እመብልዕ ፡ ወስቴ ፡ በበ ሊያትክሙ ፡ ወሰትዮትክሙ ፡ በውስተ ፡ ቤተ ፡



ቦታ ፡ የሚዘዋወር ፡ ይሁን ።
፯ በስ ፡ ፶፯ ። በደስ ፡ ፳፱ ። ከእርሱ ፡ የሚጠርጉ ትን ፡ የመሠውያውን ፡ አመድ ፡ በፈሳሽ ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ ይጣሉት ።
፰ ረስጣ ፡ ፳፰ ። ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከተባረከ ፡ ዕቃ ፡ ወገን ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ የወርቅና ፡ የብር ፡ ዕቃም ፡ ቢሆን ፡ ሰው ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ሊሠራባቸው ፡ አይገባውም ። ይህ ፡ ሕግን ፡ ማፍረስ ፡ ነውና ። ይህን ፡ ያደረገ ፡ እንደሆነም ፡ ከተፈረደበት ፡ በኋላ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይለይ ።
፱ ረስጣ ፡ ፲፱ ፡ ከሃይማኖት ፡ የወጡ ፡ ሰዎች ፡ ዳግመኛም ፡ በምእመናን ፡ ላይ ፡ ቢነሣሡባቸው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ከመሄድ ፡ ቢከለክ ሏቸው ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ በቤቱ ፡ ይቀድስ ። በአ ንድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይሰ በሰቡ ፡ ዘንድ ፡ ባይቻል ፡ ግን ፡ እያንዳንዱ ፡ ብቻውን ፡ በያለበት ፡ ቦታ ፡ ያመስግን ፡ ያን ብብ ፡ ይጸልይ ።
፲ ዶቅ ፡ ፶፫ ፡ በተቀደሰች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በኤጲስቆጶሳት ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በምእመናን ፡ በ፩ዱ ፡ ቤት ፡ ቍርባንን ፡ አያሳርጉ ። ግንር ፡ ፯ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ላይ ፡ የተደፋፈረና ፡ በእርስዋ ፡ ዘንድ ፡ ካል ሆነ ፡ በቀር ፡ ሊደረግ ፡ የማይገባውን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሥራ ፡ የሠራ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ የተወገዘ ፡ (የተለየ ፡) ይሁን ።
፲፩ በደስ ፡ ፳፱ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ስንኳ ፡ በመሠው ያው ፡ ቦታ ፡ ውስጥ ፡ ለጸሎትና ፡ በመሠውያው፡ ፊት ፡ ለመስገድ ፡ ብቻ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አይ ቀመጥ ። ፲፱ ፡ ከምእመናንም ፡ ወገን ፡ ለአንዱ ፡ እንኳ ፡ ካህን ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ወደ ፡ መሠው ያው ፡ (መቅደስ ፡) ሊገባና ፡ ቍርባንን ፡ ሊቀ በል ፡ አይገባውም ።
፲፪ ዶቅ ፡ ፳፰ ፡ በቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውስጥና ፡ በተቀደሱት ፡ ታቦቶች ፡ አጠገብ ፡ ግብዣ ፡ ስማ ድረግ ፡ መጥራት ፡ አይገባም ። ቆሮንቶስ ፡ ፲፪ ፡ (፩ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፳-፳፪) ። የእግዚአብሔርን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አታቃሉ ፡ አንዱ ፡ የተራበ ፡ ሌላውም የሰከረ ፡ ሲሆን ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ በመ ብላታችሁና ፡ በመጠጣታችሁ ፡ ከመብልና ፡ ከመ

ክርስቲያን ፡ እንዘ ፡ እሐዱ ፡ ርኁብ ፡ ወካልኡ ፡ ስኩር ።

፲፫ ዶቅ ፡ ዘ፵ወ፬ ፡ ኢይደልዎን ፡ ለአንስት ፡ በዊአ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ወኢይጸልያ ፡ ውስቴቱ ። ፳ ፡ ወእያክውኖሙ ፡ ለሠየጥ ፡ ወለመጠወ ልባን ፡ ተማይጦ ፡ በውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

፲፬ ድስቅ ፡ ዘ፲ወ፪ ፡ ይዕቀብዎሙ ፡ ለእናቅጸ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከመ ፡ ኢይባኡ ፡ ኀቤሃ ፡ እደው ፡ እለ ፡ ኢኮኑ ፡ ምእመናነ ፡ አው ፡ ምእመናነ ፡ ውጉዛን ፡ እምስታፌ ፡ ምሥጢር ፡ ቅድስት ።

ጠዋ ፡ ወገን ፡ ምንም ፡ የሌላቸውን ፡ አታሳፍሩ ዋቸው ።

፲፫ ዶቅ ፡ ፵፬ ። ሴቶች ፡ ከመቅደስ ፡ ውስጥ ፡ ገብ ተው ፡ መጸለይ ፡ አይገባቸውም ። ፳ ። ለሻጮ ችና ፡ ለለዋጮችም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ መገበያየት ፡ አይገባቸውም ።

፲፬ ድስቅ ፡ ፲፪ ። ምእመናን ፡ ያልሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ከመቀበል ፡ የተ ወገዙ ፡ ምእመናን ፡ ወደ ፡ እርስዋ ፡ እንዳይገቡ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ በሮች ፡ ይጠብቋቸው ።

---

## አንቀጽ ፡ ዳግም ፡

በእንተ ፡ መጻሕፍት ፡ እምላካውያት ፡ ዘእምነ ፡ ተወክፈቶን ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅድ ስት ፡ ዘኍልቆሙ ፡ ፹ወ፩ ።

፲፭ ረስጣ ፡ ፸ወ፩ ፡ ረስጠብ ፡ ፶ወ፮ ፡ መጻሕፍት ፡ እንተ ፡ ተወክፈዎን ፡ ምእመናን ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መጻሕፍተ ፡ ብሉይ ፡ አሪት ፡ ፰ቱ ፡ ብሔር ። መጽሐፈ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፡ ፩ ። መጽሐፈ ፡ መሳፍንት ፡ ፩ ። መጽሐፈ ፡ ሩት ፡ ፩ ። መጽሐፈ ፡ ዮዲት ፡ ፩ ። መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ አርባዕቱ ፡ ቀዳማዊ ፡ ወዳግማዊ ፡ ፩ ፡ መጽሐፍ ፡ ጣልስ ፡ ወራብዕ ፡ ፩ ፡ መጽሐፍ ፡ ወ፪ ፡ ሕዑ ፃን ። ፪ ፡ መጻሕፍት ፡ ዘእዝራ ፡ ጸሐፊ ፡ አስ ቴር ፡ ፩ ፡ መጽሐፍ ። ጦቢያ ፡ ፩ ፡ መጽሐፍ ። ነገረ ፡ መቃብያን ፡ ፪ ፡ መጻሕፍት ። ኢዮብ ፡ ፩ ፡ መጽሐፍ ። መዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ ፩ዱ ፡ መጽሐፍ ፡ ጥበበ ፡ ሰሎሞን ፡ ፭ቱ ፡ መጻሕፍት ፡ ምሳሊ ያት ፡ ቆሐልት ፡ መኃልየ ፡ መኃልይ ፡ ጥበብ ፡ ጥበበ ፡ በጎር ።

፲፮ መጻሕፍተ ፡ ነቢያት ፡ ፲ወ፮ቱ ፡ ዐበይትስ ፡ ፬ቱ ፡ ወእሙንቱ ፡ ኢሳይያስ ፡ ወኤርምያስ ፡ ወሕዝቅ ኤል ፡ ወዳንኤል ። ንኡሳንሂ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ሆሴዕ ፡ አሞጽ ፡ ሚክያስ ፡ ኢዩኤል ፡ አብድዩ ፡ ዮናስ ፡ ናሆም ፡ እንባቆም ፡ ሶፎንያስ ፡ ሐጌ ፡ ዘካርያስ ፡ ሚልክያስ ።

፲፯ ወውፁእ ፡ እምእሉ ፡ ጥበበ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ሲራክ ፡ ለትምህርተ ፡ ሕፃናት ፡ ወካዕበ ፡ መጽሐፈ ፡ ዮሴፍ ፡ ወልደ ፡ ኮርዮን ፡ ወውእቱ ፡ መጽሐፈ ፡ መቃብያን ።

## አንቀጽ ፪ ።

በቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሊቀበሏቸው ፡ የታዘዙ ፡ ቍጥራቸው ፡ ፹፩ ፡ የሆነ ፡ ስለ ፡ አም ላካውያት ፡ መጻሕፍት ።

፲፭ ረስጣ ፡ ፹፩ ፡ ረስጠብ ፡ ፶፭ ፡ ምእመናን ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተቀበሏቸው ፡ መጻሕ ፍት ፡ ፰ቱ ፡ ብሔረ ፡ አሪት ፡ የነዌ ፡ ልጅ ፡ የኢ ያሱ ፡ መጽሐፍ ፡ ፩ ፡ የመሳፍንት ፡ መጽሐፍ ፡ ፩ ፡ የሩት ፡ መጽሐፍ ፡ ፩ ፡ የዮዲት ፡ መጽሐፍ ፡ ፩ ፡ የነገሥት ፡ መጽሐፍ ፡ መጀመሪያውና ፡ ሁለ ተኛው ፡ ፩ ፡ መጽሐፍ ፡ ሦስተኛውና ፡ አራተ ኛው ፡ ፩ ፡ መጽሐፍ ፡ ሁለቱ ፡ ሕፀፃን ፡ የጸሐፊው ፡ የዕዝራ ፡ ፪ቱ ፡ መጻሕፍት ፡ አስቴር ፡ ፩ ፡ መጽ ሐፍ ፡ ጦቢያ ፡ ፩ ፡ መጽሐፍ ፡ መቃብያን ፡ ፪ ፡ መጻሕፍት ፡ ኢዮብ ፡ ፩ ፡ መጽሐፍ ፡ የዳዊት ፡ መዝሙር ፡ ፩ ፡ መጽሐፍ ፡ የሰሎሞን ፡ ጥበብ ፡ ፭ ፡ መጻሕፍት ፡ ምሳሌ ፡ ቆሀልት ፡ መኃልየ ፡ መኃልይ ፡ ጥበብ ፡ የባጎር ፡ ጥበብ ።

፲፮ የነቢያት ፡ መጻሕፍት ፡ ፲፮ ፡ ታላላቆቹ ፡ አራት ፡ እነዚህም ፡ ኢሳይያስ ፡ ኤርምያስ ፡ ሕዝቅኤል ፡ ዳንኤል ፡ ናቸው ። ታናናሾቹም ፡ ዓሥራ ፡ ሁለት ፡ እነዚሁም ፡ ሆሴዕ ፡ አሞጽ ፡ ሚክያስ ፡ ኢዩኤል ፡ አብድዩ ፡ ዮናስ ፡ ናሆም ፡ እንባቆም ፡ ሶፎንያስ ፡ ሐጌ ፡ ዘካርያስ ፡ ሚልክያስ ፡ ናቸው።

፲፯ የሲራክ ፡ ልጅ ፡ የኢያሱ ፡ ጥበብ ፡ ለሕፃናት ፡ ትምህርት ፡ ከእሊህ ፡ የተውጣጣ ፡ ነው ። ዳግ መኛም ፡ የኮርዮን ፡ ልጅ ፡ የዮሴፍ ፡ መጽሐፍ ፡ (ዜና ፡ አይሁድ ፡) እለ ፡ እርሱም ፡ የመቃብያን ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ።

፲፰ መጻሕፍተ ፡ ሐዲስ ፡ ፬ቱ ፡ ወንጌላውያን ፡ ሰባክ
ያን ፡ ማቴዎስ ፡ ወማርቆስ ፡ ሉቃስ ፡ ወዮሐ
ንስ ። ፩ዱ ፡ መጽሐፈ ፡ አብርክሲስ ፡ መጽሐፈ ፡
ሐዋርያት ፡ ፯ቱ ፡ መልእክታት ፡ ወእምኔሆሙ ፡
ዘጴጥሮስ ፡ ፪ቱ ፡ ወዘዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ፫ቱ ፡
መልእክታት ። መልእክተ ፡ ያዕቆብ ፡ ፩ዱ ።
መልእክተ ፡ ይሁዳ ፡ ፩ዱ ። መጽሐፈ ፡ ጳው
ሎስ ፡ ፲ወ፬ቱ ፡ መልእክታት ። መጽሐፈ ፡ አቡ
ቀለምሲስ ፡ ዘዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ፩ዱ ።
፲፱ እሉንኬ ፡ ሕገጋት ፡ እንተ ፡ አዘዝናክሙ ፡ ባቲ ።
ረስጣ ፡ ፶ወ፰ ፡ ረስጠብ ፡ ፴ወ፩ ። እመቦ ፡ ብእሲ
ዘነሥአ ፡ እመጻሕፍተ ፡ ሐሰት ፡ እንተ ፡ አንበ
ርዋ ፡ ክሐድያን ፡ ወአብአ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክር
ስቲያን ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ ከመ ፡ ይእቲ ፡
መጽሐፈ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንጽሕት ፡ በእንተ ፡
ሙስና ፡ ሕዝብ ፡ ይሰደድ ።

፲፰ የሐዲስ ፡ መጻሕፍት ፡ ፬ቱ ፡ ወንጌሎች ፡ ሰባክ
ያን ፡ የሆኑ ፡ ማቴዎስ ፡ ማርቆስ ፡ ሉቃስና ፡
ዮሐንስ ፡ የሐዋርያት ፡ ሥራ ፡ ፩ ፡ የሐዋርያት ፡
መጽሐፍ ፡ ፯ ፡ መልእክታት ፡ ከእነርሱም ፡ የጴ
ጥሮስ ፡ ፪ ፡ የወንጌላዊ ፡ ዮሐንስ ፡ ፫ መልእክ
ታት ፡ የያዕቆብ ፡ መልእክት ፡ ፩ ፡ የይሁዳ ፡
መልእክት ፡ ፩ ። የጳውሎስ ፡ መጽሐፍ ፡ ፲፬ ፡
መልእክታት ፡ የወንጌላዊው ፡ የዮሐንስ ፡
ራእይ ፡ ፩ ፡ መጽሐፍ ።
፲፱ እንድትጸኑባቸው ፡ ያዘዝናችሁ ፡ መጻሕፍት ፡
እነዚህ ፡ ናቸው ። ረስጣ ፡ ፶፰ ። ረስጠብ ፡ ፴፩ ።
ከሐድያን ፡ ከአስቀመጧቸው ፡ የሐሰት ፡ መጻ
ፍት ፡ የወሰደና ፡ ንጽሕት ፡ የሆነች ፡ የእግዚአ
ሔር ፡ መጽሐፍ ፡ እንደሆነች ፡ አድርጎ ፡ ሕዝ
ብን ፡ ለማሳሳት ፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔር ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያገባ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ይለይ።

## አንቀጽ ፡ ሣልስ ፡

በእንተ ፡ ጥምቀት ፡ ወእለ ፡ ይበውኡ ፡
ኀበ ፡ አሚን ፡

፳ ጥምቀትሰ ፡ ሥሩዕ ፡ ላዕለ ፡ እደው ፡ ወአንስት ፡
ንኡሰሙ ፡ ወዐቢዮሙ ፡ በእንተ ፡ ዘይቤ ፡ እግዚ
እን ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ። ጅ ፡ "ዘኢተወልደ ፡
እማይ ፡ ወእመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኢይሬእያ ፡ ለመ
ንግሥተ ፡ እግዚአብሔር" ። ወበእንተ ፡ ዘይቤ
ሎሙ ፡ ለአርዳኢሁ ፡ "ሑሩ ፡ ወመሀሩ ፡ ኵሎ ፡
አሕዛበ ፡ ወአጥምቅዎሙ ፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወ
ልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ" ። ወቀኖናት ፡ ሥሩ
ዓት ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ።
፳፩ ድስቅ ፡ ፳ወ፩ ፡ ኢያጥምቅ ፡ ዘእንበለ ፡ ኤጲስ
ቆጶስ ፡ አው ፡ ቀሲስ ፡ ወዲያቆናትሰ ፡ ይትለ
አኩ ፡ ምስሌሆሙ ።
፳፪ ጴጥ ፡ ፬ ፡ ወኢይከውኖ ፡ ለ፩ዱሂ ፡ ከመ ፡ ያጥ
ምቅ ፡ በሕልያን ፡ ወኢይሢጥ ፡ ሀብተ ፡ መን
ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በሤጥ ።
፳፫ ድስቅ ፡ ፳ ፡ ወአንስትኒ ፡ ኢያጥምቃ ፡ መነሂ ።
፳፬ ረስጣ ፡ ፵ወ፬ ፡ ወለእመቦ ፡ ብእሲ ፡ ዘተወክፈ ፡
ጥምቀተ ፡ እምዓላውያን ፡ ኢኮነ ፡ ውእቱ ፡
ምእመነ ።
፳፭ ድስቅ ፡ ፴ወ፬ ፡ ዘኒቅያ ፡ ፳ወ፬ ፡ ኢይትወከፉ ፡

## አንቀጽ ሦስት ።

ስለ ፡ ጥምቀትና ፡ ወደ ፡ ሃይማኖት ፡ ስለ
ሚገቡ ፡ ሰዎች ።

፳ ጥምቀትስ ፡ ለወንዶችም ፡ ለሴቶችም ፡ ለትል
ቆችም ፡ ለትንሾችም ፡ የታዘዘ ፡ ነው ። ጅ ፡
ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባውና ፡ ጌታችን ፡ በወ
ንጌል ፡ ከውሀና ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ያልተወ
ለደ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ አያያ
ትም ፡ ስላለ ። (ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፭) ። ለደቀመዛሙር
ቱም ፡ ሂዱና ፡ አሕዛብን ፡ ሁሉ ፡ አስተምሩ ፡
በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ስም ፡
አጥምቋቸው ፡ ስላላቸው ። (ማቴ ፡ ፳፰ ፡ ፲፱) ።
በነዚህም ፡ ሥርዓቶች ፡ ተሠርተዋል ።
፳፩ ድስቅ ፡ ፳፩ ። ከኤጲስቆጶስ ፡ ወይም ፡ ከቄስ ፡
በቀር ፡ ማንም ፡ አያጥምቅ ። ዲያቆናት ፡ ግን ፡
ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ያገልግሉ ።
፳፪ ጴጥ ፡ ፬ ። ማንም ፡ ሰው ፡ በጉቦ ፡ ሊያጠምቅ ፡
አይገባውም ። የመንፈስ ፡ ቅዱስንም ፡ ሀብት ፡
በዋጋ ፡ አይሸጥ ።
፳፫ ድስቅ ፡ ፳ ። ሴቶች ፡ ማንንም ፡ አያጥምቁ ።
፳፬ ረስጣ ፡ ፵፬ ። ከመናፍቃን ፡ ጥምቀትን ፡ የተቀ
በለ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ እማኒ ፡ አይደለም ።
፳፭ ድስቅ ፡ ፴፬ ። ኒቅያ ፡ ፳፬ ። ወንዶች ፡ ሴቶችን ፡

እደው ፡ እንስተ ፡ ወኢእንስት ፡ እደወ ፡ እላ ፡ ይትወከፉ ፡ ተባዕት ፡ ተባዕተ ፡ ወእንስት ፡ ይትወከፉ ፡ እንስተ ።

፳፮ ረስጠብ ፡ ፻ወ፩ ፡ ወይኩን ፡ ጥምቀት ፡ ውስተ ፡ ማይ ፡ ውኂዝ ፡ እው ፡ በማይ ፡ ዘይውኅዝ ፡ ኀበ ፡ ምጥማቅ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ህየ ፡ ዓጸባ ፡ ይክዓዉ ፡ ማየ ፡ ዘረከቡ ፡ ቀዲሐሙ ፡ ኀበ ፡ ምጥማቅ ።

፳፯ ድስቅ ፡ ፻ወ፩ ፡ ዘሮሜ ፡ ፮ ፡ ወተጠምቆትነስ ፡ በማይ ፡ ውእቱ ፡ ተሳትፎትነ ፡ በሞተ ፡ ክርስቶስ ፡ ወዕርገትነሂ ፡ እምነ ፡ ማይ ፡ ውእቱ ፡ ካዕበ ፡ አምሳለ ፡ ተንሥኦትነ ፡ ምስሌሁ ።

፳፰ በስ ፡ ፺ወ፯ ፡ ወለእመ ፡ ኢተረክበ ፡ ማይ ፡ ዘይውኅጥ ፡ ርእሶ ፡ ለዘይጠመቅ ፡ ይንሣእ ፡ መጠነ ፡ ፫ቱ ፡ ሕፍን ፡ እምነ ፡ ማይ ፡ ወይሕፅብ ፡ ርእሶ ፡ በስመ ፡ ሥላሴ ።

፳፱ ግር ፡ ወለዘተክህሎ ፡ ጥምቀት ፡ በዕለተ ፡ በጽሐ ፡ ጊዜሁ ፡ ኀበ ፡ ዝንቱ ፡ ኅርየት ፡ ኢያስተድኅሮ ፡ እስከ ፡ ጌሠም ፡ ወኢይጽናሕ ፡ በእንቲአሁ ፡ ብጽሐተ ፡ ወላድያን ፡ ወኢፍቁራን ፡ ወኢያስተድኅር ፡ በምክንያተ ፡ ልብስ ፡ ዘይትሜካሕ ቦቱ ፡ ወኢይጽንሑ ፡ ጥምቀተ ፡ እስከ ፡ ይመጽእ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ እው ፡ ጳጳስ ፡ እው ፡ ኤጲስቆጳስ ፡ እው ፡ ቀሲስ ፡ ባሕቱ ፡ ዘይደልዎ ፡ መባሕት ፡ ለመልእክተ ፡ ኀይለ ፡ ጥምቀት ፡ እስመ ፡ ኀይለ ፡ ጥምቀት ፡ አሐቲ ፡ ይእቲ ፡ በዕሪና ። ወዘይትኀሠሥ ፡ በእንቲአሁ ፡ ከመ ፡ ኢይኩን ፡ ካህን ፡ ዘያጠምቆ ፡ ዘነኪር ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያን ። ይቤ ፡ በእንተ ፡ ሐራ ፡ ጥቃ ፡ ዘተግህደ ፡ ዕልወቱ ፡ ወኢይእበይ ፡ ባዕል ፡ ከመ ኢይጠመቅ ፡ ምስለ ፡ ነዳይ ፡ ወኢ ፡ እግዚእ ፡ ከመ ፡ ኢይጠመቅ ፡ ምስለ ፡ ገብር ።

፴ ረስጠብ ፡ ፻ወ፩ ። ወያዕርቅዎሙ ፡ ወያቅድሙ ፡ እጥምቆ ፡ ሕፃናት ፡ ወዘክህሉ ፡ ተናግሮ ፡ በእንተ ፡ ነፍሶሙ ፡ በባሕቲቶሙ ፡ ይትናገሩ ፡ ወለእመሰ ፡ ኢክህሉ ፡ ተናግሮ ፡ ይትናገሩ ፡ አበዊሆሙ ፡ ህየንቲሆሙ ፡ ለለ፩ዱ ፡ ፩ዱ ፡ እው ፡ እምእዝማዲሆሙ ፡ ይትናገሩ ፡ በእንቲአሆሙ ፡ ወድኅረ ፡ ያጥምቅዎሙ ፡ ለእደው ፡ ዓቢያን ፡ ወእምድኅሬሆሙ ፡ ለእንስት ፡ እንዘ ፡ ይፈትሓ ፡ ሥዕርተ ፡ ርእሶን ፡ ወኢያንብራ ፡ እንስት ፡ በእደዊሆን ፡ ወርቀ ፡ ወርቅ ፡ እንተ ፡ ላዕሌሆን ፡



ሴቶችም ፡ ወንዶችን ፡ ክርስትና ፡ እያንሱ ።
ወንዶች ፡ ወንዶችን ፡ ሴቶች ፡ ሴቶችን ፡ ያንሱ ፡ እንጂ ።

፳፮ ረስጠብ ፡ ፻፩ ። ጥምቀት ፡ በወራጅ ፡ ውሀ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ማጥመቂያው ፡ በሚፈስ ፡ ውሀ ፡ ይሁን ። በዚያ ፡ የውሀ ፡ ችግር ፡ ቢኖር ፡ ያገኙትን ፡ ውሀ ፡ ቀድተው ፡ ወደ ፡ ማጥመቂያው ፡ ያፍስሱ ።

፳፯ ድስቅ ፡ ፻፩ ። ሮሜ ፡ ፮ ። በውሀ ፡ መጠመቃችን በክርስቶስ ፡ ሞት ፡ አንድ ፡ መሆናችን ፡ ነው ። ከውሀውም ፡ መውጣታችን ፡ ሁለተኛ ፡ ከእርሱ ጋር ፡ የመነሣታችን ፡ ምሳሌ ፡ ነው ። (ሮሜ ፡ ፮ ፡ ፫-፭ ።)

፳፰ በስ ፡ ፺፯ ። የሚጠመቀውን ፡ ሰው ፡ ራስ ፡ የሚያጠልቅ ፡ ውሀ ፡ ባይገኝ ፡ እፍኝ ፡ ያህል ፡ ውሀ ፡ ወስዶ ፡ በሥላሴ ፡ ስም ፡ ራሱን ፡ ያጥምቀው ።

፳፱ ግር ። ጊዜው ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ለመጠመቅ ፡ የተቻለውን ፡ ሰው ፡ ለነገ ፡ አያሳድረው ። የወላጆችን ፡ ወይም ፡ የወዳጆችን ፡ መምጣት ፡ አይጠብቅ ። በሚመካበትም ፡ ልብስ ፡ ምክንያት ፡ አያዘግየው ። ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወይም ፡ ጳጳስ ፡ ኤጲስቆጳስ ፡ ወይም ፡ ቄስ ፡ ሳይመጣ ፡ አናጠምቅም ፡ አይበሉ ። የማጥመቅ ፡ ሥልጣን ያለው ፡ ያጥምቀው ፡ እንጂ ። የጥምቀት ፡ ሥልጣን ፡ በትክክል ፡ አንዲት ፡ ናትና ። ስለ ፡ እርሱ ፡ የሚፈለገውስ ፡ የሚያጠምቀው ፡ ካህን ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተለየ ፡ እንዳይሆን ፡ ነው ፡ ክህደቱ ፡ ስለታወቀው ፡ ስለ ፡ ሐራ ፡ ጥቃ ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ባለጸጋ ፡ ከድሀ ፡ ጋር ፡ አልጠመቅም ፡ አይበል ። ጌታም ፡ ከባሪያ ፡ ጋር ፡ አልጠመቅም ፡ አይበል ።

፴ ረስጠብ ፡ ፻፩ ። ልብሳቸውን ፡ አስወልቀው ፡ ሕፃናቱን ፡ አስቀድመው ፡ ያጥምቋቸው ። እምነትን ፡ ለመናገር ፡ የቻሉት ፡ ራሳቸው ፡ ይናገሩ ። ለመናገር ፡ ካልቻሉ ፡ ግን ፡ ወላጆቻቸው ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ ለእያንዳንዳቸው ፡ ይናገሩላቸው ። ወይም ፡ ዘመዶቻቸው ፡ ስለነርሱ ፡ ይናገሩ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ታላላቆቹን ፡ ወንዶች ፡ ያጥምቋቸው ። ከነርሱም ፡ ቀጥሎ ፡ የራሳቸውን ፡ ጠጕር ፡ ፈትተው ፡ ሴቶቹን ፡ ያጥምቋቸው ። ሴቶች ፡ ሲጠመቁ ፡ በእጃቸው ፡ ላይ ፡

ወኢያውርድ ፡ ፩ሂ ፡ ምንተኒ ፡ ነኪረ ፡ ምስሌሁ ፡ ኀበ ፡ ማይ ።

፴፩ በደስ ፡ ፲ወ፱ ፡ ወእለሂ ፡ ይጠመቁ ፡ ይትሐፀቡ ፡ በማይ ፡ በዕለተ ፡ ሐሙስ ፡ እምነ ፡ ሰባዔ ፡ ወይብልዑ ፡ ወይጹሙ ፡ በዕለተ ፡ ዓርብ ። ወለ እመ ፡ ተዳደቃ ፡ ወረከባ ፡ ለብእሲት ፡ ደመ ፡ ትክቶ ፡ ትጽናሕ ፡ እስከ ፡ ትነጽሕ ። ወበዕለተ ፡ ሰንበት ፡ ያስተጋብኦሙ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ለእለ ፡ ይጠመቁ ፡ ወየእዝዞሙ ፡ ከመ ፡ ያድንኑ ፡ አር እስቲሆሙ ፡ መንገለ ፡ ምሥራቅ ። ወይሰፋሕ ፡ እዴሁ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ወይጸሊ ። ወሶበ ፡ ፈጸመ ፡ አምሕሎቶሙ ፡ ይነፋሕ ፡ ውስተ ፡ ገጸቲሆሙ ፡ ወይዕትብ ፡ አባሎሙ ፡ በዘይከውኑ ፡ ትጉሃነ ፡ በኵሉ ፡ ነገር ፡ ቅዱስ ፡ ወጸሎታት ። ወያቅም ዎሙ ፡ ጊዜ ፡ ንቅወተ ፡ ዶርሆ ፡ ኀበ ፡ ማየ ፡ ምጥማቅ ፡ ወኤጲስቆጶስ ፡ ይጸሊ ፡ ላዕለ ፡ ቅብዐ ፡ ዘይት ፡ ዘቦቱ ፡ ያምሕሉ ፡ ወየሀቦ ፡ ለቀሲስ ፡ ወይቁም ፡ መንገለ ፡ ፀጋሙ ፡ ወይጸሊ ፡ ላዕለ ፡ ዘይተ ፡ ቅብዓት ፡ ዘውእቱ ፡ ቅብዐ ፡ እኰቴት ፡ ወየሀቦ ፡ ለካልእ ፡ ቀሲስ ፡ ወያቅሞ ፡ መንገለ ፡ የማኑ ። ወዘያጠምቅዎሂ ፡ ይሚጥ ፡ ገጾ ፡ እም ሥራቅ ፡ መንገለ ፡ ምዕራብ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡ ወይክሕዶ ፡ ለዲያብሎስ ። ወ፩ዱ ፡ ቀሲስ ፡ የአ ኀዞ ፡ እዴሁ ፡ ዘየማን ፡ ወይሚጥ ፡ ገጾ ፡ መን ገለ ፡ ምሥራቅ ፡ በአንጻረ ፡ ማይ ፡ ወእምቅድመ ርደቱ ፡ ውስተ ፡ ማይ ፡ ይትአመን ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ምእመን ፡ በአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመን ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወከመዝ ፡ ይጠመቁ ። ወድኅረ ፡ ይትመጠዉ ፡ ቍርባነ ፡ ወኢይጥዐሙ ፡ ምን ተኒ ፡ እንበለ ፡ ይንሥኡ ፡ ምሥጢራተ ፡ ቅድ ሳት ። ወከማሁ ፡ ካልአንኒ ፡ እለ ፡ ጾሙ ፡ ምስሌ ሆሙ ። ወሶበሰ ፡ ተፈጸመ ፡ ቅዳሴ ፡ ሎሙ ፡ ሥልጣን ፡ ከመ ፡ ይብልዑ ፡ ዘፈቀዱ ። በስ ፡ ፻ወ፰ ፡ ወይትመጠዉ ፡ ቍርባነ ፡ እምቅድመ ፡ ሕዝብ ።

፴፪ ሥርዋጽ ፡ ፩ዱ ፡ እምቀኖናት ፡ ወዘኮነ ፡ ሎቱ ፡ ወልድ ፡ ወልደ ፡ ዓመት ፡ ዘይልዕል ፡ ወኢያጥ መቆ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ካህነ ፡ ይትከላእ ፡ እምተል እኮት ። ወለአመ ፡ ኮነ ፡ ሕዝባዌ ፡ ይስደድ ፡ እምቍርባን ፡ ወኢይመጥውዎ ፡ ቍርባነ ፡ እስከ



የወርቅ ፡ ጌጥ ፡ አያድርጉ ፤ ከጌጡ ፡ አንድስ ፡ እንኳ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ወደ ፡ ውሀው ፡ አያውርድ ።

፴፩ በደስ ፡ ፲፱ ። የሚጠመቁትም ፡ ሰዎች ፡ በሱባዔው ፡ ውስጥ ፡ በጸሎተ ፡ ሐሙስ ፡ ዕለት ፡ በውሀ ፡ ይታጠቡና ፡ ይብሉ ፤ በዕለተ ፡ ዓርብ ፡ ግን ፡ ይጹሙ ። ሴቲቱን ፡ የግዳጅ ፡ ደም ፡ ቢመ ታት ፡ እስከትነጻ ፡ ድረስ ፡ ትቈይ ። ኤጲስቆጶስ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ የሚጠመቁትን ፡ ሰብስቦ ፡ ራሳቸውን ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ እንዲያዘነብሉ ፡ ይዘዛቸው ። እጁንም ፡ በላያቸው ፡ ዘርግቶ ፡ ይጸልይ ። መሐላውን ፡ እስምሎ ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ በፊታቸው ፡ ላይ ፡ እፍ ፡ ይበልባቸው ። በተቀደሰ ፡ ነገር ፡ ሁሉና ፡ በጸሎትም ፡ የተጉ ፡ በሚሆኑ ፡ ገንዘብ ፡ አካላቸውን ፡ አማትቦ ፡ ይባርክ ። በዶሮ ፡ ጩኸት ፡ ጊዜ ፡ በመጠመቂያው ፡ ቦታ ፡ ያቁማቸው ። ኤጲስቆጶሱም ፡ መሐላ ፡ በሚያስምልበት ፡ በዘይቱ ፡ ቅብዓት ፡ ላይ ፡ ይጸልይ ። ለቄሱም ፡ ይስጠው ። በግራ ውም ፡ ይቁም ፡ ይኸውም ፡ ቅብዐ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ። በዘይቱም ፡ ቅብዓት ፡ ላይ ፡ ይጸልይ ፤ ለሁለተኛውም ፡ ቄስ ፡ ይስጠው ። በቀኙም ፡ ያቁመው ። የሚያጠምቁትም ፡ ልጅ ፡ ፊቱን ፡ ከምሥራቅ ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ መልሶ ፡ በሰማይ ፡ አንጻር ፡ ዲያብሎስን ፡ ይካደው ። አንዱ ፡ ቄስም ፡ ቀኝ ፡ እጁን ፡ ይዞ ፡ በውሀው ፡ አንጻር ፡ ፊቱን ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ይመልሰው ። ወደ ፡ ውሀ ፡ ከመውረዱም ፡ በፊት ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ያመነ ፡ መሆኑን ፡ ያረጋ ግጥ ። እንዲህ ፡ አድርገው ፡ ይጠመቁ ። ከዚ ሀም ፡ በኋላ ፡ ይቍረቡ ። ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ሳይቀበሉ ፤ ምንም ፡ ምን ፡ አይቅመሱ ። እንደ ፡ እነርሱ ፡ የጾሙት ፡ ሌሎቹም ፡ እንዲሁ ፡ ያድ ርጉ ። ቅዳሴው ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላም ፡ የወደዱ ትን ፡ እንዲበሉ ፡ መብት ፡ አላቸው ። በስ ፡ ፻፰ ። እነርሱም ፡ ከሕዝቡ ፡ አስቀድሞ ፡ ይቍ ረቡ ።

፴፪ ሥርዋጽ ፡ ፩ ። ከቀኖናት ፡ የተገኘ ። ዓመት ፡ የሞላው ፡ ልጅ ፤ ከዚያም ፡ ያለፈ ፡ ልጅ ፡ ኖሮት፡ ያላጠመቀው ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፤ ካህን ፡ ቢሆን ፡ ከማገልገል ፡ ይከልከል ። መሃይምን ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ከሥጋውና ፡ ከደሙ ፡ ይለይ ። እስኪያጠ

ያጠምቆ ።

፴፫ ቀጠግ ፡ ዘ፮ ፡ ወለፅኑሳት ፡ ኢይክልእዎን ፡ እምተጠምቆ ፡ በአይኒ ፡ ጊዜ ፡ ዘፈቀዳ ፡ ወአልቦ ፡ ማእከለ ፡ ወላዲት ፡ ወወልዳ ፡ ተሳትፎ ፡ በጥምቀተ ፡ ክርስትና ። ዳእሙ ፡ ለኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይክሥት ፡ አሚኖቶ ፡ በባሕቲቱ ።

፴፬ ሥርዊጽ ፡ ፪ቱ ፡ ወዘተረፈ ፡ እምቀኖናት ፡ ይነግር ፡ ከመ ፡ ለሕፃን ፡ ለእመ ፡ ይፈርሁ ፡ በእንቲአሁ ፡ ሞተ ፡ እምቅድመ ፡ ንጽሓ ፡ ለወላዲቱ ፡ እምደመ ፡ ሐርሳ ፡ ለያብእዎ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወያጥምቅዎ ፡ ምስለ ፡ ካልእታ ።

፴፭ ድስቅ ፡ ፴ወ፬ ፡ ወይቅብዓ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ርእሳ ፡ ለብእሲት ፡ ወዘተርፈ ፡ አባላ ፡ ትቅብዓ ፡ ዲያቆናዊት ። እስመ ፡ ኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይነጽር ፡ ብእሲ ፡ ዕርቃነ ፡ ብእሲት ። ወነዋ ፡ ተሠርዐ ፡ ዝንቱ ፡ ሕግ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅብጣዊት ፡ በመጽሐፈ ፡ ጥምቀት ፡ እንተ ፡ ባሕቲቱ ፡ ዘአስተጋብእዎ ፡ እምቀኖናት ፡ ዘይነግር ፡ ክዋኔሃ ፡ ለጥምቀተ ፡ ክርስትና ። ወኵሎሙ ፡ ጸሎታተ ፡ እለ ፡ እሙራን ፡ ባቲ ። ወቦቱ ፡ ያጠምቅዎ ፡ ወይደሉ ፡ ከመ ፡ ይዕቀብዎ ፡ በዐቢይ ፡ ጥንቃቄ ።

፴፮ ረስጣ ፡ ፵ወ፫ ፡ ወለዘሂ ፡ ተደለወ ፡ ለተጠምቆ ፡ ይሕትቱ ፡ ግብሮ ።

፴፯ በደስ ፡ ፲ወ፱ ፡ ከመ ፡ በዘመን ፡ ዘተገሠፀ ፡ ቦቱ ፡ ዘተደለዉ ፡ ለተጠምቆ ፡ ለይትኃሠሡ ፡ በእንተ ፡ ገድሎሙ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ፈጸሙኑ ፡ ኵሎ ፡ ሠናያተ ። ወለእመ ፡ ስምዐ ፡ ኮንዎሙ ፡ እለ ፡ እምጽእዎሙ ፡ ከመ ፡ እሙንቱ ፡ ገብሩ ፡ ዘንተ ፡ ያስምዕዎሙ ፡ ቃለ ፡ ወንጌል ፡ እምይእቲ ፡ ዕለት ፡ ዘእምጽእዎሙ ፡ ባቲ ። ወለእመ ፡ በጽሐ ፡ ዕለት ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ያጠምቅዎሙ ፡ ያምሕሎሙ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ለኵሎሙ ፡ ለለ ፡ እሐዱ ፡ እለ ፡ ኮኑ ፡ ሰምዐ ፡ በእንቲአሆሙ ፡ ከመ ፡ ያእምር ፡ እመ ፡ ንጹሓን ፡ እሙንቱ ። ወለእመ ፡ ተረክበ ፡ አሐዱ ፡ ዘኢኮነ ፡ ንጹሐ ፡ ይትፈለጥ ፡ ወይትገኀሥ ። እስመ ፡ ኢሰምዐ ፡ ውእቱ ፡ ቃለ ፡ በአሚን ።

ምቀውም ፡ ድረስ ፡ ቍርባንን ፡ እይሰጡት ።

፴፫ ቀጠግ ፡ ፮ ። የፀነሱትን ፡ ሴቶች ፡ በወደዱት ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ከመጠመቅ ፡ እይከልክሏቸው ። በእናትና ፡ በልጅዋ ፡ መካከል ፡ በጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ እንድነት ፡ የለም ። ለሰው ፡ ሁሉ ፡ በየራሱ ፡ እምነቱን ፡ እንዲገልጽ ፡ ይገባዋል ፡ እንጂ ።

፴፬ ሥርዋጽ ፡ ፪ ። እናቱ ፡ ከእራስነት ፡ ደም ፡ ከመንጻትዋ ፡ አስቀድሞ ፡ ይሞታል ፡ ብለው ፡ የሚፈሩትን ፡ ሕፃን ፡ በሞግዚት ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አግብተው ፡ ማጥመቅ ፡ እንዲገባ ፡ ከቀኖናት ፡ የቀረውን ፡ ይናገራል ።

፴፭ ድስቅ ፡ ፴፬ ። ኤጲስቆጶስ ፡ የሴቲቱን ፡ ራስ ፡ ይቅባ ፡ የቀረውን ፡ ሰውነቷን ፡ ግን ፡ ዲያቆናዊት ፡ ትቅባት ፡ ወንድ ፡ የሴትን ፡ ዕርቃን ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ አይገባምና ። የጥምቀትን ፡ ሁናቴና ፡ በእርስዋ ፡ የታወቁትን ፡ ጸሎታት ፡ ከሚናገሩት ፡ መጻሕፍት ፡ በሰበሰቡት ፡ በቅብጣዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መጽሐፈ ፡ ጥምቀት ፡ ውስጥ ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ እነሆ ፡ ተጻፈ ። በእርሱ ፡ ያጥምቁት ። በትልቅ ፡ ጥንቃቄም ፡ ይጠብቁት ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ።

፴፮ ረስጣ ፡ ፵፫ ። ለመጠመቅ ፡ የተዘጋጀውን ፡ ሰው ፡ ግብሩን ፡ ይመርምሩት ።

፴፯ በደስ ፡ ፲፱ ። ለአመክሮ ፡ በተወሰነላቸው ፡ ዘመን ፡ በጎ ፡ ነገርን ፡ ሁሉ ፡ ፈጽመዋልን ፡ እያሉ ፡ ስለ ፡ ገድላቸው ፡ ይመርምሩ ። ያመጧቸው ፡ ሰዎች ፡ እነርሱ ፡ ይህን ፡ እንደ ፡ ሠሩ ፡ ምስክር ፡ ቢሆኑዋቸው ፡ ከእመጧቸው ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ የወንጌልን ፡ ቃል ፡ ያሰሟቸው ። የሚያጠምቁበትም ፡ ቀን ፡ ቢደርስ ፡ ስለነርሱ ፡ የመሰከሩትን ፡ ሁሉ ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ያምላቸው ። ንጹሖች ፡ እንደሆኑ ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ። ንጹሕ ፡ ያልሆነ ፡ እንድ ፡ ቢገኝ ፡ ፈጽሞ ፡ ይለይ ። እርሱ ፡ ቃሉን ፡ በሃይማኖት ፡ እልተረዳምና ።

# አንቀጽ ፡ ራብዕ ፡

በእንተ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ።

፴፰ ወመብዝኅተ ፡ ነገሮሙ ፡ ለኤጲስቆጶሳት ፡ በይደልዎሙ፡ ለሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ እስመ ፡ ይሰመይ፡ ውእቱ ፡ በውስተ ፡ ካልእን ፡ አምቀኖናት ፡ ዘኤጲስቆጶሳት ፡ ዐቢየ ፡ ወቀዳማዌ ፡ ወርእሰ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ወውእቱ ፡ ፪ቱ ፡ አክፋል ፡ ሀልው ፡ እመጽሐፍ ፡ ወልብ ።

፴፱ ቀዳማዊ ፡ እመጻሕፍት ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳትሰ ፡ ውእቶሙ ፡ ተላውያነ ፡ ክርስቶስ ፡ ወሐዋርያቲሁ ፡ ዘይቤሎሙ ፡ "ዘኪያክሙ ፡ ተወክፈ ፡ ኪያየ ፡ ተወክፈ" ። ለሊቀ ፡ ጳጳሳትሰ ፡ ሊቅናሁ፡ ላዕለ ፡ መሢሓውያን ፡ ክመ ፡ ምስፍና ፡ ሙሴ ፡ ላዕለ ፡ እስራኤል ፡ ወማኅበረ ፡ ቅዱሳን ።

፵ ዘኒቅያ ፡ ፴ወ፰ቱ ፡ አዘዙ ፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ ሊቃነ፡ ጳጳሳት ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ፡ ፬ቱ ፡ ባሕቲቶሙ ፡ ከመ ፡ ፬ቱ ፡ መጻሕፍተ ፡ ወንጌል ፡ ወ፬ ፡ አፍላጋት ፡ ወ፬ ፡ ሥርዓተ ፡ ዓለም ፡ ወ፬ ፡ መዓዝኒሃ ፡ ወ፬ ፡ ነፋሳት ፡ ወ፬ ፡ ጠባይዐ ፡ ፍጥረታት ።

፵፩ ወይኩን ፡ ሊቀ ፡ እምኔሆሙ ፡ ወመኰንነ ፡ በዓለ ፡ መንበረ ፡ ጴጥሮስ ፡ ዘሮምያ ፡ በከመ ፡ አዘዙ ፡ ሐዋርያት ። ወአምድኅሬሁ ፡ በዓለ ፡ እስክንድርያ ፡ ዐባይ ፡ ወውእቱ ፡ መንበረ ፡ ማርቆስ ። ወሣልስ ፡ በዓለ ፡ ኤፌሶን ፡ ውእቱ ፡ መንበረ ፡ ዮሐንስ ፡ ቴዎሎጎስ ። ወራብዕ ፡ በዓለ ፡ መንበረ ፡ አንጾኪያ ፡ ወውእቱ ፡ መንበረ ፡ ጴጥሮስ ፡ ካዕበ ።

፵፪ ወይትፈለጡ ፡ ኵሎሙ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ አምታሕተ ፡ እደዊሆሙ ፡ ለአሉ ፡ ፬ቱ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ወይኩን ፡ ኵሉ ፡ ጳጳስ ፡ አምአላ ፡ አህጉር ፡ ዐበይት ፡ ይሢም ፡ ኤጲስቆጶሳተ ፡ ዘአድያሚሁ፡ አምታሕተ ፡ እደዊሆሙ ፡ ለጳጳሳት ። ወኢያጳጽሶ ፡ ሎቱስ ፡ እሐዱኒ ፡ እምኤጲስቆጶሳቲሁ ። እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይትሌዐል ፡ እምኔሆሙ ። ወይዕቀብ ፡ ኵሉ ፡ ብእሲ ፡ ሥርዓቶ ፡ ወኢይትዐ

# አንቀጽ አራት ።

ስለ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ።

፴፰ ለሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ የሚገባውን ፡ የኤጲስቆጶሳትን ፡ አብዛኛውን ፡ ነገር ፡ ይናገራል ። በኤጲስቆጶሳት ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ ታላቅና ፡ መጀመሪያ ፡ የኤጲስቆጶሳትም ፡ አለቃ ፡ ይባላልና ። ይኸውም ፡ ከመጽሐፍና ፡ ከልብ ፡ የተገኙ ፡ ሁለት ፡ ክፍሎች ፡ አሉት ።

፴፱ መጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ ከመጻሕፍት ፡ የተገኘው ፡ ነው ። ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ግን ፡ የክርስቶስና ፡ እናንተን ፡ የተቀበለ ፡ እኔን ፡ መቀበሉ ፡ ነው ፡ ያላቸው ፡ የሐዋርያት ፡ ተከታዮች ፡ ናቸው ። ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በክርስቲያኖች ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ሹመቱ ፡ ሙሴ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ እንደ ነበረው ፡ ምስፍና ፡ ያለ ፡ ነው ።

፵ ኒቅያ ፡ ፴፰ ። ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ በዓለም ፡ ሁሉ ፡ ውስጥ ፡ አራት ፡ ብቻ ፡ እንዲሆኑ ፡ በኒቅያ ፡ የተሰበሰቡ ፡ የቅዱሳን ፡ ማኅበር ፡ አዘዙ ። እንደ ፡ ፬ቱ ፡ የወንጌል ፡ መጻሕፍትና ፡ እንደ ፡ ፬ቱ ፡ ወንዞች ፡ እንደ ፡ ፬ቱ ፡ ሥርዓታተ ፡ ዓለም ፡ እንደ ፡ ፬ቱ ፡ ማዕዝነ ፡ ዓለም ፡ እንደ ፡ ፬ቱ ፡ ነፋሳት ፡ እንደ ፡ ፬ቱ ፡ የፍጥረት ፡ ጠባዮች ።

፵፩ ከእነርሱም ፡ የሮሙ ፡ የጴጥሮስ ፡ በዓለ ፡ መንበር ፡ ሐዋርያት ፡ እንዳዘዙ ፡ አለቃ ፡ ፈራጅም ፡ ይሁን ። ከእርሱም ፡ ቀጥሎ ፡ የታላቂቱ ፡ የእስክንድርያ ፡ በዓለ ፡ መንበር ፡ ይሁን ፡ ይኸውም ፡ የማርቆስ ፡ መንበር ፡ ነው ። ሦስተኛውም ፡ የኤፌሶን ፡ በዓለ ፡ መንበር ፡ ነው ፡ ይኸውም ፡ የነባቤ ፡ መለኮት ፡ የዮሐንስ ፡ መንበር ፡ ነው ። አራተኛው ፡ የአንጾኪያው ፡ በዓለ ፡ መንበር ፡ ነው ፡ ይኸውም ፡ የጴጥሮስ ፡ ሁለተኛው ፡ መንበር ፡ ነው ።

፵፪ ኤጲስቆጶሳት ፡ ሁሉ ፡ በነዚህ ፡ በአራቱ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ሥልጣን ፡ በታች ፡ ሆነው ፡ ይለዩ ። ጳጳስ ፡ ሁሉ ፡ ከእሊህ ፡ ከታላላቆቹ ፡ አገሮች ፡ የተሾመ ፡ ይሁን ፡ ከጳጳሳት ፡ ሥልጣን ፡ በታች ፡ የሆኑትን ፡ የየአውራጃውን ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ይሹም ፡ ዘንድ ። እርሱን ፡ ግን ፡ ከኤጲስቆጶሳቶቹ ፡ አንዱ ፡ አንኳ ፡ አያጳጽሰው ። እርሱ ፡ ከእነርሱ ፡ ይበልጣልና ። ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሥርዓ

ደው ፡ ኀበ ፡ ሥርዓተ ፡ ካልኡ ። ወዘዐለወ ፡ ዘንተ ፡ ሕገ ፡ እንተ ፡ ሠራዕናሃ ፡ ሲኖዶስ ፡ ያወግዞ ።

ዘ፴ወ፰ ፡ ወትፍልስ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ኤፌሶን ፡ ኀበ ፡ ሀገረ ፡ ንጉሥ ፡ ከመ ፡ ትኩን ፡ ዛቲ ፡ ክብረ ፡ ለነገሥት ፡ ወለካህናት ፡ ኅቡረ ። ወያክብርዎ ፡ ለኤጲስቆጶሰ ፡ ዚአሃ ፡ ወኢያስተሐቅርዎ ፡ በእንተ ፡ ተግኅሦ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስናሁ ፡ እምኔሁ ። ወያክብርዎ ፡ በሰም ፡ ሀቢይ ፡ ዘካቶሊካ ፡ ዘውእቱ ፡ ስመ ፡ ሊቃናት ።

ወያዕብይዎ ፡ ካዕበ ፡ ለበዓለ ፡ መንበረ ፡ ተሰሎንቄ ፡ እስመ ፡ ከመዝ ፡ ይደሉ ።

ወኢይግርር ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘኢየሩሳሌም ፡ ለካልኡ ፡ እምኤጲስቆጳሳት ፡ አላ ፡ ያዕብይዎ ፡ ፈድፋደ ፡ ወያክብርዎ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ሥዩም ፡ ላዕለ ፡ ሀገር ፡ ቅድስት ፡ ወበእደዊሁ ፡ ሀሎ ፡ መስቀለ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወመካነ ፡ ትንሣኤሁ ።

ወያክብርዎ ፡ ካዕበ ፡ ለበዓለ ፡ መንበረ ፡ በግዳድ ፡ ዘውእቱ ፡ ሰልቅ ፡ እንተ ፡ ውስተ ፡ ብሔረ ፡ ምሥራቅ ፡ ወይእቲ ፡ ትሰመይ ፡ ሀገረ ፡ ምድያም ። ወያዕብይዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ካዕበ ፡ በስመ ፡ ሊቃናት ፡ ወያብሕዎ ፡ ሎቱኒ ፡ እምይእዜ ፡ ከመ ፡ ያጵጵስ ፡ ጳጳሳተ ፡ በከመ ፡ ይገብሩ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ከመ ፡ ኢይጻምዉ ፡ ምሥራቃውያን ፡ በሐዊሮቶሙ ፡ ኀበ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳተ ፡ እንጾኪያ ፡ በእንተ ፡ መፍቅዶሙ ። እው ፡ በተመይጠቶሙ ፡ እምኀቤሁ ። እስመ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳተ ፡ እንጾኪያ ፡ ነዋ ፡ ሠምረ ፡ በዝንቱ ፡ እምድኅረ ፡ ሰአልዎ ፡ ሎቱ ፡ ጉባኤ ፡ ማኅበር ፡ ከመ ፡ ኢይኅዝን ፡ በእንተ ፡ ዘተአተተ ፡ እምኔሁ ፡ ሥልጣነ ፡ ምሥራቅ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ኢኀሠሠ ፡ ዘንተ ፡ ግብረ ፡ ዘእንበለ ፡ ከመ ፡ ያብእሙ ፡ ውስተ ፡ ዕረፍት ፡ ለክርስቲያን ፡ ዘብሔረ ፡ ፋርስ ።

ዘ፴ወ፱ ፡ ወለእመ ፡ መጽአ ፡ ግብር ፡ ዘይትጋብኡ ፡ ቦቱ ፡ ኤጲስቆጳሳት ፡ ውስተ ፡ ብሔረ ፡ ሮም ፡ ወመጽአ ፡ ኀቤሆሙ ፡ በዓለ ፡ ዛቲ ፡ ሢመት ፡ ዘውእቱ ፡ በዓለ ፡ ሰልቅ ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ እምርት ፡ ሀገረ ፡ በግዳድ ። እስመ ፡ ይእቲ ፡ አመ ፡ ቀዳሚ ፡ ክነ ፡ ትሰመይ ፡ ሳቡር ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ዮምሰ ፡ ምድያም ። ለይትለ



ቱን ፡ ይጠብቅ ። ወደ ፡ ሌላም ፡ ሥርዓት ፡ እይ
ተላለፍ ። ይህችን ፡ የሠራናትን ፡ ሕግ ፡ ያፈረሰ
ውን ፡ ሲኖዶስ ፡ ያወግዘዋል ።
፺፫ ኒቅያ ፡ ፴፰ ። የኤፌሶን ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ለካህ
ናቱና ፡ ለነገሥታቱ ፡ በእንድነት ፡ ክብር ፡
ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ከተማ ፡ (ወደ ፡
ቍስጥንጥንያ፡) ትዛወር ። በእርስዋ ፡ የተሾመ
ውንም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ያክብሩት ። ሊቀ ፡ ጵጵ
ስናው ፡ ከእርሱ ፡ ስለሄደ ፡ እያቃልሉት ። ካቶ
ሊክስ ፡ በሚባለውም ፡ በታላቅ ፡ ስም ፡ ያክብ
ሩት ። ይኸውም ፡ የሊቃናት ፡ ስም ፡ ነው ።
፺፬ ዳግመኛም ፡ የተሰሎንቄውን ፡ በዓለ ፡ መንበር ፡
ያክብሩት ፤ እንዲህ ፡ ሊሆን ፡ ይገባልና ።
፺፭ የኢየሩሳሌሙ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ከኤጲስቆጳሳት ፡
ለሌላው ፡ እይታዘዝ ። እርሱን ፡ ፈጽመው ፡ ያክ
ብሩት ፡ እንጂ ። በቅድስት ፡ ሀገር ፡ በኢየሩሳ
ሌም ፡ የተሾመ ፡ ነውና ። በእጁም ፡ የጌታችን ፡
የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መስቀልና ፡ የትንሣኤዉ ፡
ቦታ ፡ አለና ።
፺፮ ዳግመኛም ፡ በምሥራቅ ፡ ክፍል ፡ የምትገኘው ፡
ሰልቅ ፡ የምትባለውን ፡ የበግዳድን ፡ በዓለ ፡
መንበር ፡ ያክብሩት ። ይህችውም ፡ የምድያም ፡
እገር ፡ ትባላለች ። ይህንንም ፡ ዳግመኛ ፡ በሊቃ
ናት ፡ ስም ፡ ያክብሩት ። ለእርሱም ፡ ሊቃነ ፡
ጳጳሳት ፡ እንደሚሠሩት ፡ ሁሉ ፡ ጳጳሳትን ፡ እን
ዲሾም ፡ ይፍቀዱለት ። የምሥራቅ ፡ ሰዎች ፡
የፈለጉትን ፡ ነገር ፡ ለማግኘት ፡ ወደ ፡ እንጾኪ
ያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በመሄድና ፡ ከእርሱም ፡
ዘንድ ፡ በመመለስ ፡ እንዳይደክሙ ። የእንጾ
ኪያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ የምሥራቅ ፡ ሥልጣን ፡
ከእርሱ ፡ በመወገድ ፡ እንዳያዝን ፡ ሠለስቱ ፡
ምእት ፡ ከለመኑት ፡ በኋላ ፡ እነሆ ፡ በዚህ ፡ ተሰ
ማምቷል ። የፋርስን ፡ እገር ፡ ክርስቲያኖች ፡
ወደ ፡ ዕረፍት ፡ ሊያገባቸው ፡ ወደደ ፡ እንጂ ፡
እርሱ ፡ ይህን ፡ ክብር ፡ እልፈለገምና ።

፺፯ ኒቅያ ፡ ፴፱ ። ኤጲስቆጳሳት ፡ በሮም ፡ የሚሰበሰ
ቡበት ፡ ሥራ ፡ ቢመጣ ፤ የዚችም ፡ ሹመት ፡
ባለቤት ፡ ወደነርሱ ፡ ቢመጣ ፤ ይኸውም ፡ በግ
ዳድ ፡ በመባል ፡ የታወቀችው ፡ የሰልቅ ፡ በዓለ ፡
መንበር ፡ ነው ፡ እርስዋ ፡ ቀድሞ ፡ ሳቡር ፡
ትባል ፡ ነበርና ፤ ዛሬ ፡ ግን ፡ ምድያም ፡ ትባላ
ለች ። በእቀማመጥ ፡ ከሮም ፡ ጳጳሳት ፡ ሁሉ ፡

ሀል ፡ ወይከበር ፡ ውስተ ፡ መንበር ፡ መልዕልተ ፡ ኵሎሙ ፡ ጳጳሳተ ፡ ሮም ፡ ኅቡረ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ በመዓርገ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘውስተ ፡ ብሔረ ፡ ምሥራቅ ፡ ወይኩን ፡ መንበሩ ፡ ውስተ ፡ መዓርግ ፡ ሳብዕት ፡ እምድኅረ ፡ ኤጲስ ቆጶስ ፡ ዘኢየሩሳሌም ። ወለኵሉ ፡ ዘዐሰወ ፡ ዘንተ ፡ ሕገ ፡ ሲኖዶስ ፡ ያወግዞ ።

፴፰ ዘ፴ ። ወኢያበውሕዎሙ ፡ ሲኖዶስ ፡ ዐቢይ ፡ ከመ ፡ ይትጋብኡ ፡ በብሔረ ፡ ስልቅ ፡ ከመ ፡ ያንብሩ ፡ ሕገጋተ ፡ ዘእንበለ ፡ በመባሕተ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘአንጾኪያ ። እስመ ፡ ሰእመ ፡ ኮነ ፡ ሊቆሙ ፡ በመዓርገ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በእንተ ፡ ዘኮነ ፡ ተባይጾተ ፡ አልቦሙ ፡ መባሕት ፡ ከመ ፡ ይፍትሑ ፡ ወይእስሩ ፡ ሕገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወኢከመ ፡ ይወስኩ ፡ ውስቴታ ፡ አው ፡ ያሕጽጹ ፡ በምክረ ፡ ርእሶሙ ፡ አላ ፡ ይኩኑ ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡ ግብር ፡ ግሩራነ ፡ ለሊቃናት ፡ ወለማኅበረ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ።

፴፱ ሥርዋጽ ፡ ፫ ፡ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ መንበር ፡ ረሰዩ ፡ ሊቀ ፡ ጽጽስና ፡ ዘኤፌሶን ፡ ሰበዓለ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ ወረሰይዎ ፡ ዳግማዌ ፡ በመዓርጊሁ ፡ ወኮነ ፡ እምሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእስክንድርያ ሣልሳዩ ።

፵ ፴ወ፪ ። ወሰብአ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ኢይሚሙ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ እማእምራኒሆሙ ፡ ወኢበሥምረተ ፡ ርእሶሙ ። እስመ ፡ ጳጳሶሙ ፡ ይከውን ፡ እምታሕተ ፡ እዴሁ ፡ ለበዓለ ፡ እስክንድርያ ፡ ወውእቱ ፡ ዘይደልዎ ፡ ይሚም ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ሊቀ ፡ እምነቤሁ ፡ ዘውእቱ ፡ መትሕተ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ።

፵፩ ወሶበ ፡ ተሠይመ ፡ ጽጽስና ፡ ዝንቱ ፡ ዘዝኩር ፡ በስመ ፡ ሊቃናት ፡ ኢብውሕ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ያጽጽስ ፡ ጳጳሳተ ፡ በከመ ፡ ያጽጽሱ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ዳዕሙ ፡ ውእቱ ፡ ባሕቲቱ ፡ ይክብር ፡ በስመ ፡ ሊቀ ፡ ጽጽስና ፡ ዘእንበለ ፡ ይኩን ፡ ሎቱ ፡ ሥልጣን ፡ ዝንቱ ። ወሰእመ ፡ ኮነ ፡ ግብር ፡ ዘይትጋብኡ ፡ ቦቱ ፡ ጉባኤ ፡ በምድረ ፡ ሮም ፡ ወመጽአ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ዝንቱ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሰይንበር ፡ ውስተ ፡ መንበር ፡ ሳምን ፡ እምድኅረ ፡ በዓለ ፡ ስልቅ ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ እም አህጉረ ፡ አድያም ፡ ዘውስቴቶን ፡ ባቢሎን ፡ ወእልዕራቅ ፡ ወመንግሥተ ፡ ሳቡር ፡ እስመ ፡ አብሕዎ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይሚም ፡ ኤጲስቆጶሳተ ፡



በላይ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ በአንድነት ፡ ይክበር ። እርሱ ፡ በምሥራቅ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ በሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ማዕርግ ፡ ነውና ። መንበሩም ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ኢጲስቆጶስ ፡ በኋላ ፡ ሰባተኛ ፡ ማዕርግ ፡ ይሁን ። ይህን ፡ ሕግ ፡ ያፈረሰውንም ፡ ሲኖዶስ ፡ ያወግዘዋል ።

፴፰ ኒቅያ ፡ ፴ ። ያለ ፡ አንጾኪያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ፈቃድ ፡ ሕጎችን ፡ ለመወሰን ፡ በስልቅ ፡ ሀገር ፡ ይሰበሰቡ ፡ ዘንድ ፡ ትልቁ ፡ ሲኖዶስ ፡ አይፈቅድላቸውም ። አለቃቸው ፡ መተካከልን ፡ ስለፈለገ ፡ በሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ማዕርግ ፡ ቢሆንም ፡ እንኳ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሕግ ፡ ሊያስሩ ፡ ሊፈቱ ፡ ወይም ፡ በራሳቸው ፡ ምክር ፡ በውስጥዋ ፡ ሊጨምሩም ፡ ሊያሳንሱም ፡ ሥልጣን ፡ የላቸውምና ። በሥራ ፡ ሁሉ ፡ ለአለቆችና ፡ ለማኅበረ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ የተገዙ ፡ ይሁኑ ፡ እንጂ ።

፴፱ ሥርዋጽ ፡ ፫ ። ከዚህም ፡ መንበር ፡ በኋላ ፡ የኤፌሶንን ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ለቍስጥንጥንያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አደረጉ ። በማዕርግም ፡ ሁለተኛ ፡ አደረጉት ። የእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳትም ፡ ሦስተኛ ፡ ሆነ ።

፵ ኒቅያ ፡ ፴፪ ። የኢትዮጵያ ፡ ሰዎች ፡ ከሀዋቂዎቻቸው ፡ ወገን ፡ በራሳቸውም ፡ ፈቃድ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳትን ፡ ለራሳቸው ፡ አይሹሙ ። ጳጳሳቸው ፡ ከእስክንድርያው ፡ በዓለ ፡ መንበር ፡ ሥልጣን ፡ በታች ፡ ነውና ። ከሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በታች ፡ የሆነውን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ከእርሱ ፡ ወገን ፡ ሊሾምላቸው ፡ የሚገባውም ፡ እርሱ ፡ ነው ።

፵፩ ይህ ፡ በሊቃናት ፡ ስም ፡ የተጠራውም ፡ ጵጵስናን ፡ በተሾመ ፡ ጊዜ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ እንደሚሾሙ ፡ ጳጳሳትን ፡ ይሾም ፡ ዘንድ ፡ አይገባውም ። የመሾም ፡ ሥልጣን ፡ ሳይኖረው ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ በሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ስም ፡ ይከበር ፡ እንጂ ። በሮም ፡ ጉባኤ ፡ የሚሰበሰቡበት ፡ ሥራ ፡ ቢኖር ፡ ይህ ፡ ኢትዮጵያዊም ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ቢመጣ ፡ ከስልቅ ፡ በዓለ ፡ መንበር ፡ በኋላ ፡ በስምንተኛው ፡ መንበር ፡ ይቀመጥ ። ይህችውም ፡ የሳቡር ፡ መንግሥትና ፡ የእልዕራቅ ፡ የባቢሎንም ፡ አውራጃዎች ፡ ክፍል ፡ ናት ። ለአውራጃዎቹ ፡ ኢጲስቆጶሳትን ፡ እንዲሾም ፡ ፈቅደውለታልና ። ኢጲስቆጶሳትም ፡ በራሳ

ለአድያመ ፡ ዚአሁ ። ወኢ ብውሕ ፡ ሎሙ ፡ ከመ ፡ ይሚምዎ ፡ በርእሶሙ ፡ ኤጲስቆጶሳት ።

፴፪ ዘ፴ወ፬ ፡ ወይርአይ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡ ግብር ፡ ወትእዛዝ ፡ ዘይገብርዎ ፡ ጳጳሳቲሁ ፡ ወኤጲስቆጶሳቲሁ ፡ ውስተ ፡ በሐውርቲሆሙ ፡ እንተ ፡ ተውህቦሙ ፡ ላዕሌሆሙ ። ወለእመ ፡ ረከበ ፡ ዲበሆሙ ፡ ምንተኒ ፡ ግብረ ፡ ዘኢይደሉ ፡ ለይወልጦ ፡ ወየአዝዝ ፡ ውስቴቱ ፡ በዘተርእየ ። እስመ ፡ ውእቱ ፡ አቡሆሙ ፡ ለኵሎሙ ። ወእሙንቱኒ ፡ ውሉዱ ፡

፴፫ ወጳጳስሰ ፡ ዘሥዩም ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ያክብሩ ፡ ኪያሁ ፡ ከመ ፡ እኁ ፡ ዐቢይ ፡ ዘተሠይመ ፡ ላዕለ ፡ እኅዊሁ ፡ ወመፍትው ፡ ይትአዘዙ ፡ ሎቱ ፡ በእንተ ፡ ሥነ ፡ መራሕቱ ፡ ወሠረዮቱ ።

፴፬ ወሊቀ ፡ ጳጳሳትኒ ፡ ከመ ፡ አብ ፡ በሥልጣኑ ፡ ላዕለ ፡ ውሉዱ ፡ ወበከመ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ቦቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ወሥልጣን ፡ ላዕለ ፡ ዘታሕተ ፡ እዴሁ ፡ ከማሁ ፡ ለበዓለ ፡ መንበረ ፡ ሮምያ ፡ ቦቱ ፡ ሥልጣን ፡ ላዕለ ፡ ኵሎሙ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ሊቅ ፡ ከመ ፡ ጴጥሮስ ፡ ዘኮነ ፡ ሎቱ ፡ ሥልጣን ፡ ላዕለ ፡ ኵሎሙ ፡ ሊቃነ ፡ ክርስቲያን ፡ ወማኅበረ ፡ ሰብእ ። እስመ ፡ ውእቱ ፡ ህየንተ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእነ ፡ ላዕለ ፡ ሕዝቡ ፡ ወአብያተ ፡ ክርስቲያናቲሁ ።

፴፭ ዘ፴ወ፫ ፡ ወይትጋብኡ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ኵሉ ፡ አህጉር ፡ ኀበ ፡ ጳጳሶሙ ፡ ፪ተ ፡ ጊዜ ፡ በበዓመት ፡ ከመ ፡ ይርአዩ ፡ ዘይደሉ ፡ በእንቲአሁ ። ወኪያሁ ፡ ለነጽሮ ፡ ከመ ፡ ትኩን ፡ እውሥአቶሙ ፡ ጽንዕተ ፡ እመ ፡ ዕለት ፡ ግርምት ፡ በዘአክሀልዎሙ ፡ ኀይለ ።

፴፮ ዘ፴ወ፮ ፡ ወከማሁ ፡ ጳጳሳትኒ ፡ ወኤጲስቆጶሳት ፡ ይትጋብኡ ፡ ኀበ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሶሙ ፡ ምዕረ ፡ በበ ዓመት ፡ በእምሳለ ፡ ውእቱ ፡ በከመ ፡ ኮኑ ፡ ሰብአ ፡ መሳፍንተ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ያመ ርጉ ፡ ኀበ ፡ ሙሴ ፡ ኵሎ ፡ ዘዐጸቦሙ ።

፴፯ ረስጣ ፡ ዘ፩ ፡ ወኢይትፌጸም ፡ ሢመቱ ፡ ለሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእንበለ ፡ በህላዌሆሙ ፡ ለጉባኤ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ወመጥሮጶሊስ ፡ ዘውእቱ ፡ ጳጳስ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ በእንተ ፡ ሢመቱ ፡ ጋእዝ ፡ ይግበሩ ፡ በምክሮሙ ፡ ለእለ ፡ ይበዝኁ ፡ እምኔ



ቸው ፡ ሊሾሙት ፡ አይገባቸውም ።

፴፪ ኒቅያ ፡ ፴፬ ። ጳጳሳቱና ፡ ኤጲስቆጶሳቱ ፡ በተሾሙ ባቸው ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ትእዛዝና ፡ ሥራ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ይመልከት ። በእነርሱም ፡ ላይ ፡ ማናቸውንም ፡ የማይገባ ፡ ሥራ ፡ ሲሠሩ ፡ቢያገኝ ፡ ይለውጠው ። የተገለ ጠለትንም ፡ ይዘዝ ። እርሱ ፡ ለሁሉም ፡ አባታ ቸው ፡ ነውና ፡ እነርሱም ፡ ልጆቹ ፡ ናቸውና ።

፴፫ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ የተሾመውን ፡ ጳጳስ ፡ ግን ፡ በወንድሞቹ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተሾመ ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡ ወንድም ፡ ያክብሩት ፡ መሪና ፡ አስተ ዳዳሪ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ መጠን ፡ ሊታዘዙለት ፡ ይገባል ።

፴፬ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱም ፡ አባት ፡ በሥልጣኑ ፡ በልጆቹ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ ያህል ፡ ነው ። ሊቀ ፡ ጳጳ ሳት ፡ ከሥልጣኑ ፡ በታች ፡ ባሉት ፡ ላይ ፡ ትእዛ ዝና ፡ ሥልጣን ፡ አለው ። እርሱ ፡ በክርስቲያ ኖች ፡ አለቆችና ፡ በሰዎች ፡ ማኅበር ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ እንዳለው ፡ እንደ ፡ ጴጥሮስ ፡ አለቃ ፡ ነውና ። እርሱ ፡ በሕዝቡና ፡ በአብያተ ፡ ክርስቲያናቱ ፡ ላይ ፡ የጌታችን ፡ የክርስቶስ ፡ ምትክ ፡ ነው ።

፴፭ ኒቅያ ፡ ፴፫ ። የአገሩ ፡ ሁሉ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ስለእርሱ ፡ የሚገባውን ፡ ይመረምሩ ፡ ዘንድ ፡ እርሱንም ፡ ለማየት ፡ በየዓመቱ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ከጳጳሳቸው ፡ ዘንድ ፡ ይሰብሰቡ ። ስለ ፡ ተሰጣ ቸው ፡ ሥልጣን ፡ በምታስፈራዪቱ ፡ ቀን መልሳቸው ፡ የጸናች ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ።

፴፮ ኒቅያ ፡ ፴፮ ። እንዲሁም ፡ ጳጳሳትና ፡ ኤጲስቆጶ ሳት ፡ ሰብዓው ፡ የደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ መሳፍ ንት ፡ የቸገራቸውን ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ሙሴ ፡ ያቀ ርቡ ፡ እንደነበረ ፡ በዚሁ ፡ አምሳል ፡ በየመቱ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከሊቀ ፡ ጳጳሳቸው ፡ ዘንድ ፡ ይሰብ ሰቡ ።

፴፯ ረስጣ ፡ ፩ ። የሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ሹመት ፡ የኤጲስ ቆጶሳትና ፡ የመጥሮጶሊስ ፡ (ይኸውም ፡ ጳጳስ ፡ ማለት ፡ ነው ።) ጉባኤ ፡ ሳይሆን ፡ አይፈጸምም ። ስለ ፡ ሹመቱ ፡ ጠብ ፡ ክርክር ፡ ቢሆን ፡ በድ

ሆሙ ። ወእምዝ ፡ ዘይደልዎ ፡ ይሠየም ፡ ላዕሌሆሙ ።

፻፰ ዘኒቅያ ፡ ዘ፴ወ፯ ፡ ወለይትአዘዝ ፡ በዓለ ፡ ኵሉ ፡ ሀገር ፡ ወብሔር ፡ እመኒ ፡ ኮነት ፡ ዐባየ ፡ እው ፡ ንእስተ ፡ ዘትከውን ፡ ታሕተ ፡ እደ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ይሥርው ፡ በረከተ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በአምጣነ ፡ ትከል ፡ ወይፈንዉ ፡ ኪያሃ ፡ ኀቤሁ ፡ በበኵሉ ፡ ዓመት ፡ ከመ ፡ ይትረዳእ ፡ ባቲ ፡ ወዝንቱ ፡ አንቀጽ ፡ ዘእንበለ ፡ ግዘት ።

፻፱ ዘ፵ወ፱ ፡ ኢ.ብውሕ ፡ ለጳጳስ ፡ ወለኤጲስቆጶሳቲሁ ፡ ሐቲተ ፡ አበሳቲሁ ፡ ለዘአበስ ፡ እምኤጲስቆጳሳት ፡ እለ ፡ ታሕተ ፡ እዴሁ ፡ ወፈቲሐ ፡ ፍትሕ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወኢተወከፎተ ፡ ንስሓሁ ፡ ዘእንበለ ፡ መባሕተ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ምስሌሆሙ ፡ ወበአእምሮቱ ፡ ወትእዛዘ ፡ ዚአሁ ።

፻፲ ዘ፱ ፡ ወኢይትወከፉ ፡ ላዕለ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ውጼተ ፡ አሐዱ ፡ ጳጳስ ፡ ምንትኒ ፡ እምጳጳሳቲሁ ፡ እለ ፡ ታሕተ ፡ እዴሁ ፡ አው ፡ ለእመ ፡ ተረከበ ፡ በላዕሌሁ ፡ ምንትኒ ፡ እምአበሳት ፡ ዘእንበለ ፡ ይምጻእ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ካልእ ፡ እምአኃዊሁ ፡ እም፫ቲሆሙ ፡ ወነጽሮቶሙ ፡ ግብሮ። ወኢይደሉ ፡ ለአሐዱሂ ፡ እምሠለስቲሆሙ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ለአስተዋድዮ ፡ ከመ ፡ ያብሑ ፡ ሎቱ ፡ በእንተ ፡ ውእቱ ፡ አው ፡ ይስነአዉ ፡ ላዕሌሁ ፡ ዘእንበለ ፡ መባሕተ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ካልእ ፡ እምአኃዊሁ ፡ ወነጽሮቶሙ ፡ ግብሮ ፡ በከመ ፡ አቅደምነ ፡ ነጊረ ።

፻፲፩ ዘ፱ወ፩ ፡ ወኢይደሉ ፡ ለአሐዱሂ ፡ እምሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ወጳጳሳት ፡ ወኤጲስቆጳሳት ፡ ከመ ፡ ይፍታሕ ፡ ዘአሰሮ ፡ ካልኡ ፡ ዘእንበለ ፡ እምድኅረ ፡ ሞቱ ። ወሊቀ ፡ ጳጳሳትሰ ፡ ብዉሕ ፡ ውእቱ ፡ እምድኅረ ፡ ተከሥቶ ፡ ከመ ፡ ይፍታሕ ፡ ማእሰሮሙ ፡ ለእሉ ፡ ኵሎሙ ፡ ሰበ ፡ ርእየ ፡ ዝከተ ። እስመ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ እግዚእ ፡ ቤት ፡ በላዕሌሆሙ ፡ ወላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ክቡር ።

፻፲፪ ዘ፸ወ፯ ፡ ወለእመ ፡ ሜመ ፡ ጳጳስ ፡ አሐደ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እምኤጲስቆጳሳት ፡ ለይፈኑ ፡ ምስሌሁ ፡ ካዕበ ፡ ኮሬ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ከመ ፡ ያብእ ፡ ሎቱ ፡ ኀበ ፡ ሀገሩ ፡ ወቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ወያንብሮ ፡ በዕለት ፡ ቀዳሚት ፡ ጊዜ ፡ በአቲ ፡ ዲበ ፡ መንበር ፡ ወሰበ ፡ ነበረ ፡ ውስተ ፡ ሀገሩ ፡ ፫ተ ፡

ምዕ ፡ ብልጫ ፡ ያድርጉት ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የሚገባው ፡ በላያቸው ፡ ይሾም ።

፻፰ ኒቅያ ፡ ፴፯ ። ከተማውና ፡ ባላገሩ ፡ ሁሉ ፡ ይታዘዝ ። በሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ሥልጣን ፡ በታች ፡ ያለች ፡ አገር ፡ ታላቅም ፡ ታናሽም ፡ ብትሆን ፡ ለሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ የሚሰጥ ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ የምትችለውን ፡ ያህል ፡ ይሥሩባት ። በእርስዋም ፡ ይረዳባት ፡ ዘንድ ፡ በያመቱ ፡ ወደእርሱ ፡ ይላኩዋት ። ይህ ፡ አንቀጽ ፡ ውግዘት ፡ የሌለበት ፡ ነው ።

፻፱ ኒቅያ ፡ ፵፱ ። ለጳጳስና ፡ ለኤጲስቆጶሳቱ ፡ ከሥልጣኑ ፡ በታች ፡ ካሉት ፡ ከኤጲስቆጶሳቱ ፡ ወገን ፡ የበደለውን ፡ በደል ፡ መመርመርና ፡ በእርሱም ፡ መፍረድ ፡ በሊቀ ፡ ጳጳሳቱም ፡ ፈቃድ ፡ ካልሆነና ፡ እውቆ ፡ ካላዘዘ ፡ በቀር ፡ ንስሐ ፡ መቀበል ፡ አይገባቸውም ።

፻፲ ኒቅያ ፡ ፱ ። በሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ላይ ፡ ከሥልጣኑ ፡ በታች ፡ ካሉት ፡ ከጳጳሳቱ ፡ ወገን ፡ የሚቀርበውን ፡ የአንዱን ፡ ጳጳስ ፡ ነገረ ፡ ሥራ ፡ (ክስ) ፡ ምንም ፡ አይቀበሉ ። ከበደል ፡ ወገን ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ቢገኝም ፡ ከሦስቱ ፡ ወንድሞቹ ፡ ሌላው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ሳይመጣና ፡ ሥራውን ፡ ሳይመረምሩ ፡ አይቀበሉ ። ከሦስቱ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳትም ፡ ለአንዱ ፡ እንኳ ፡ እርሱን ፡ ለማጣላት ፡ እንዲያስናብተው ፡ ወይም ፡ እንዲስማሙበት ፡ ሊያደርግ ፡ አይገባውም ። አስቀድመን ፡ እንደ ፡ ተናገርን ፡ ሥራውን ፡ ከመመርመራቸውና ፡ ከወንድሞቹ ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ በሌላው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ፈቃድ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ።

፻፲፩ ኒቅያ ፡ ፱፩ ። ከሊቃነ ፡ ጳጳሳትና ፡ ከጳጳሳት ፡ ከኤጲስቆጶሳትም ፡ ለአንዱስ ፡ እንኳ ፡ ሌላው ፡ ያወገዘውን ፡ መፍታት ፡ አይገባውም ። ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ እንጂ ። ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ግን ፡ ይህን ፡ በመረመረ ጊዜ ፡ ከተገለጠለት ፡ በኋላ ፡ የሁሉንም ፡ ግዝት ፡ ሊፈታ ፡ ሥልጣን ፡ አለው። እርሱ ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ባለቤት ፡ ነውና ፡ በሁሉም ፡ ላይ ፡ ክቡር ፡ ነውና ።

፻፲፪ ኒቅያ ፡ ፸፯ ። ጳጳሱ ፡ ከኤጲስቆጶሳት ፡ ወገን ፡ አንዱን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ቢሾም ፡ ወደ ፡ ሹመት ፡ ሀገሩና ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያስገባው ፡ ዘንድ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ኮሬ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ (ቆሞስ) ፡ ይላክ ። በገባ ፡ ጊዜም ፡ በዕለተ ፡ ቀዳሚት ፡ በወንበሩ ፡ ያስቀምጠው ። በአገሩ ፡

አውራኅ ፡ ይሑር ፡ ኀበ ፡ ጳጳስ ፡ የሐውጾ ፡ በእንተ ፡ እምኖቱ ፡ ወየእዝዞ ፡ ጳጳስ ፡ ለኵሉ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አው ፡ ለርእሰ ፡ ካህናት ፡ አው ፡ ለርእሰ ፡ ዲያቆናት ፡ ይፍትንዎ ፡ ሕገገ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጳሳት ፡ ወቈመቶ ፡ ላዕለ ፡ ውሳኔያተ ፡ እሉ ፡ ኵሎሙ ። ወለእመ ፡ ረከብዎ ፡ ዘንዋ ፡ በቀበሙ ፡ ፍጹመ ፡ አሚሃ ፡ ያስተጽንዕ ፡ ግብሮ ፡ ወያብሖ ፡ ሎቱ ፡ ቀዊመ ፡ በኤጲስቆጶስናሁ ፡ ወይትወከፉ ፡ ትእዛዛቲሁ ። ወከማሁ ፡ ካዕበ ፡ ለይግበሩ ፡ ጳጳሳት ፡ በሊቃነ ፡ ጳጳሳቲሆሙ ። እሌ ፡ ሎቱ ፡ ለዘየዐሉ ፡ ዘንተ ፡ ሕገ ፡ ወሲኖዶስ ፡ ያወግዞ ።

ሦስት ፡ ወር ፡ ከተቀመጠ ፡ በኋላ ፡ እጅ ፡ ለመንሳት ፡ ወደ ፡ ጳጳሱ ፡ ይሂድ ። ጳጳሱም ፡ የኤጲስቆጳሳትን ፡ ሕግጋት ፡ መፈጸሙንና ፡ በእነርሱም ፡ መጽናቱን ፡ ይፈትኑት ፡ ዘንድ ፡ ቆሞሱን ፡ ወይም ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱን ፡ ወይም ፡ ሊቀ ፡ ዲያቆናቱን ፡ ይዘዝ ። ፈጽሞ ፡ ጠብቋቸው ፡ ቢያገኙት ፡ ያንጊዜ ፡ ሥራውን ፡ ያጽናለት ። በኤጲስቆጶስነቱም ፡ እንዲጸናና ፡ ትእዛዞቹን ፡ እንዲቀበሉት ፡ ያሠልጥነው ። ጳጳሳትም ፡ ስለ ሊቃነ ፡ ጳጳሳቶቻቸው ፡ እንዲሁ ፡ ያድርጉ ። ይህን ፡ ሕግ ፡ ለሚያፈርስ ፡ ሰው ፡ ወዮለት ። ሲኖዶስም ፡ (ጉባኤ) ፡ ያወግዘዋል ።

፳፫ ዘኒቅያ ፡ ፵ወ፱ ፡ ወኢይትበዋሕ ፡ አሐዱኒ ፡ እምኤጲስቆጳሳት ፡ እለ ፡ ታሕተ ፡ እደዊሆሙ ፡ ለጳጳሳት ፡ እምኀበ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በምንትኒ ፡ ዘእንበለ ፡ በትእዛዘ ፡ ጳጳሰሙ ፡ ወእጠዩቆቶ ፡ በዝንቱ ፡ ወኢይኅሥሥ ፡ መኑሂ ፡ እምጳጳሳት ፡ ወእምኤጲስቆጳሳት ፡ በዊአ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ዘእንበለ ፡ መባሕተ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ። ወለኵሉ ፡ ዘዐለወ ፡ ዘንተ ፡ ሲኖዶስ ፡ ያወግዞ ።

፳፫ ኒቅያ ፡ ፵፱ ። ከጳጳሳት ፡ ሥልጣን ፡ በታች ፡ ካሉት ፡ ከኤጲስቆጳሳት ፡ ወገን ፡ አንዱ ፡ እንኳ ፡ ጳጳሳቸው ፡ ሳያዝና ፡ ሳይፈቅድ ፡ ወደ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ሊሄድ ፡ አይገባውም ። ከጳጳሳትና ፡ ከኤጲስቆጳሳትም ፡ ወገን ፡ ማንም ፡ ቢሆን ፡ ያለ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ፈቃድ ፡ ከንጉሥ ፡ ዘንድ ፡ መግባትን ፡ አይፈልግ ። ይህን ፡ ሕግ ፡ ያፈረሰውን ፡ ሁሉ ፡ ሲኖዶስ ፡ ያወግዘዋል ።

፳፬ ረስጠጅ ፡ ፳ወ፩ ፡ ወኤጲስቆጳሳተ ፡ ኵሉ ፡ አሮ ያም ፡ ይደልዎሙ ፡ ከመ ፡ ያእምሩ ፡ መኑ ፡ ውእቱ ፡ ሊቆሙ ፡ ወይረስይዎ ፡ ሎሙ ፡ ከመ ፡ ርእስ ፡ ወኢይግበሩ ፡ ምንተኒ ፡ ግብረ ፡ ዐቢየ ፡ ወንኡሰ ፡ ዘእንበለ ፡ በምክሩ ፡ ወውእቱኒ ፡ ካዕበ ፡ ኢይግበር ፡ ግብረ ፡ ዐቢየ ፡ ዘእንበለ ፡ በምክረ ፡ ኤጲስቆጳሳት ፡ ኵሎሙ ፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ በአሐዱ ፡ ኅብረት ።

፳፬ ረስጠጅ ፡ ፳፩ ። የአውራጃው ፡ ሁሉ ፡ ኤጲስቆጳሳት ፡ አለቃቸው ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ ማወቅ ፡ ይገባቸዋል ። እንደ ፡ አለቃም ፡ ያድርጉት ። ታላቅ ፡ ታናሽም ፡ ሥራ ፡ እርሱን ፡ ሳያማክሩ ፡ አይሥሩ ። እርሱም ፡ ደግሞ ፡ ያለ ፡ ኤጲስቆጳሳቱ ፡ ምክር ፡ ታላቅ ፡ ሥራ ፡ አይሥራ ። ሁሉም እንዲህ ፡ በአንድ ፡ስምምነት ፡ ይሁኑ ።

፳፭ ዳግማዊኒ ፡ ልዑናዊ ። ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ህየንተ ፡ ክርስቶስ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ በእንተ ፡ ሀቂበ ፡ ሃይማኖት ፡ ወመግቦተ ፡ መሃይምናን ፡ በግብር ፡ ሕጋዊት ፡ መንፈሳዊት ። ወቀዳሚት ፡ ዘይቀውሙ ፡ ባቲ ፡ ትእዛዝ ፡ ሥሩዕ ፡ ላዕለ ፡ መሃይምናን ፡ ወድልው ፡ ላዕለ ፡ ኵሎሙ ፡ ወያኤምር ፡ በእንቲአሁ ፡ ሕግ ፡ ወከዊነ ፡ ማእዝ ። ቀዳማዊስ ፡ በእንተ ፡ ዘተሠይመ ። ወዳግም ፡ በእንተ ፡ ማእዝ ፡ ጠባይዕ ፡ ዘለባውያን ፡ ከመ ፡ ይኅሥሡ ፡ ሊቀ ፡ ዘይመርሖሙ ፡ ኀበ ፡ እእምሮ ፡ ፍኖተ ፡ ጽድቅ ፡ ወገቢረ ፡ ሠናይ ፡ ወእምተወፍዮት ፡ ኀበ ፡ ርእስ ፡ ዘይከልእሙ ፡ እምሀምያት ። ወይፈትሕ ፡ ማእከሌሆሙ ፡ በእንተ ፡ ተጋእዞተ ፡ ወተጻልአት ።

፳፭ ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ከልብ ፡ የኑቃ ፡ ነው ። ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ሃይማኖትን ፡ ስለ ፡ መጠበቅና ፡ ምእመናንን ፡ በመንፈሳዊና ፡ በሕጋዊ ፡ ሥራ ፡ ለማስተዳደር ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ። ሹመቱ ፡ የሚጸናበትም ፡ ትእዛዝ ፡ በምእመናን ፡ ላይ ፡ ተሠርታለች ። በሁሉ ፡ ላይም ፡ ተዘጋጅታለች ። ስለእርሱም ፡ ሕግና ፡ ልማድ ፡ ያስረዳል ። መጀመሪያው ፡ ስለ ፡ ተሾመው ፡ ይናገራል ። ሁለተኛውም ፡ ስለ ፡ አዋቂዎች ፡ ልማዳዊ ፡ ጠባይ ፡ የሚናገር ፡ ነው ። ወደ ፡ እውነት ፡ መንገድና ፡ ወደ ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ የሚመራቸውን ፡ አለቃ ፡ ይፈልጉ ፡ ዘንድ ። ከበደል ፡ የሚከለክላቸው፣ በጠብና ፡ በክርክር ፡ ጊዜ ፡ በመካከላቸው ፡ የሚፈርድ ፡ አለቃ ፡ ከመቀበላቸው ፡ የተነሣ ።

፲፯ ወሶበ ተሰይመ ዘይደልዎ ይትረከብ ቀዊም በትእዛዝ : ወይሌልወት ላዕለ : ሰብእ እለ የኀርዩ ፈደፋደ ። ከመ ይኅረዩ ሊቀ ለሕዝብ ። ወትእዛዛትስ : ድልዋት : ላዕለ : ሰብእ እለ የኀርዩ : ፫ቱ ጾታ እማንቱ : እሑቲ እምኔሆን እእምሮ ርትዕ : እንተ ዘከርነ ውስተ አንቀጸ ሰማዕት ። ወካልእ ታኒ : አእምሮ : ከመ : ይብጽሑ : በቱ : ኀበ : ጥያቄ : አእምሮቱ : ለዘትይደልዎ : ዛቲ : ሢመት : ወሣልሰታ : ከመ : ያጥርዩ : ምክረ : ወጥበበ : እለ : ይመርሑ : ኀበ : ኅሪዮቱ : ለዘመኑ : ውእቱ : ዘይበቍዕ : ለሰብእ : ዝንቱ : መዋ ዕል : ወዘይኄይስ : ለሕግ : ወምርሖቶሙ : ዘያ ቀውም : ወይኤምር ።

፲፰ ወትእዛዛት ለዘይደልዎ ሎቱ ፪ቱ ክፍል እመጻሕፍት : ወነዋ : ተዘክረት : በውስተ : ቀዳሚት : አንቀጽ : ኤጲስቆጶስ ። ወበእንተ : ልቡናሁ : ወይእቲ : ፬ቱ : ጾታ ። ቀዳሚሃ : ሰላም : ወድኅነት ልብ : ወአባል እንተ ኢይትከሃል : ዘእንበሌሆን : ተዋም : በሊቅና : ዘውእቶን : ርእይ : ወሰገሀን : ወልሳን : ወአእ ዳው : ወእእጋር ። ወእምዝኒ : ድኅነት : እም ደዌያት : ዘትከልእ : እምተራክቦ : ምስለ : ሰብእ : ሢመቱ : ዘከመ : ዝልጋሴ : ወለምጽ ። ወራብዕታ : በዘይትፌጸም : ሥርዓተ : አመግቦ : ወበቍዔታት : ሥነ : ግእዝ : ወሥነ : ምክር : ወአመክሮ : ወጥበብ ።

፲፱ ወእምከመ ረከቡ ሰብእ ኅሪየት ብዙኃነ ሰብእ : ዘትትረከብ : ውስቴቶሙ : ሥርዓተ : ዛቲ : ሢመት : ይደሉ : ከመ : ይኅረይዎ : ለዘ ፍጹም : እምኔሆሙ : በሥርዓታቲሃ : ወለዘየፈ ጥኑ : ሰብእ : ለተአዝዞቱ : ብዙኀ ። ወለእመ : አበየ : ውእቱ : እምኔሃ : ወኢተወክፋ : ለይኅ ረዩ : እምኔሆሙ : ካልአ ። ወለእመ : ኢኮነ : ካልኡ : ድልወ : ኢመፍትው : ይኅድግዎ ። ወለእመ : ተረክቡ : ፪ቱ : እለ : ዕሩያን : በሥር ዓታቲሃ : ያቅርቡ : ወይሚምዎ : ለዘይልህቅ : እምኔሆሙ : በእንተ : ፍድፋዴ : መዋዕል ። ወባሕቱ : እስመ : ልሂቀ : መዋዕል : ለገቢረ :



፲፯ የሚገባው : በተሾመ : ጊዜም : በትእዛዝ : መጽናት : ይደረጋል ። ለሕዝቡ : አለቃን ይመርጡ : ዘንድ : ስለሚመርጡ : ሰዎች : ፈጽሞ : አግባብ : አላቸው ። ለመራጮችም : ትእዛዞች : ተዘጋጅተውላቸዋል ። እነርሱም : ሦስት : ወገን : ናቸው ። ከእነርሱ : አንዲቱ : በአንቀጸ : ሰማዕት : የተናገርናት : የቀናች : እውቀት : ናት ። ሁለተኛዪቱም : ለዚህ ሹመት : የሚበቃውን : ወይ : ማመን : የምታ ደርስ : እውቀት : ናት ። ሦስተኛዪቱም : ለዘ መኑ : የሚስማማውን : ወይ : መምረጥ : የሚ መሩትን : ጥበብንና : ምክርን : ያገኙ : ዘንድ : ነው ። እርሱም : በዘመኑ : ለሚኖሩ : ሰዎች : የሚጠቅም : ሕግን : ለመጠበቅና : ለማስተ ማር : የሚስማማ : የሚያጸናና : የሚያስረዳ : ነው ።

፲፰ ለእርሱ : የሚገቡትም : ትእዛዞች : ከመጻሕ ፍት : ፪ : ክፍሎች : ናቸው ። እነሆ : በአንቀጸ : ኤጲስቆጶሳት : በመጀመሪያው : ተነገረች ። ስለ : አእምሮውም : ተነግራለች ። እርስዋም : አራት : ወገን : ናት ። መጀመሪያዋ : ያለነርሱ : በሹመት : ጸንቶ : መኖር : የማይቻል : የአካ ልና : የልብ : ድኅነት : ሰላም : ናቸው ። እነር ሱም : ዓይን : ጆሮ : አንደበት : እጆችና : እግ ሮች : ናቸው ። ከዚህም : በኋላ : ከተሾመባ ቸው : ሰዎች : ጋር : መገናኘትን : ከምትከለክ ለው : ደዌ : መዳን : ነው ። ይህም : እንደ : ደዌ ሥጋ : እንደ : ለምጽ : ያለ : ነው ። አራተኛ ዋም : የአስተዳደር : ሥነ : ሥርዓትና : ጥቅም : በጎ : ምግባር : በጎ : ምክርና : ጥበብ : ፍጹም : የሚሆንበትን : ትናገራለች ።

፲፱ መራጮች : የዚህች : ሹመት : ሥርዓት : የም ትገኝባቸውን : ብዙ : ሰዎች : ቢያገኙ : በሥር ዓትዋ : ከነርሱ : ፍጹም : የሆነውንና : ሰዎች : ብዙ : ጊዜ : ፈጥነው : የሚታዘዙለትን : ሊመር ጡት : ይገባል ። የተመረጠውም : እምቢ : ብሎ : ባይቀበላት : ከነርሱ : ሌላውን : ይም ረጡ ። ሌላው : በቂ : ሆኖ : ባይገኝ : ሊተዉት : አይገባም ። በሥርዓቶቿ : ሁለቱም : ተካክ ለው : ቢገኙ : ከነርሱ : በዘመን : የሚበልጠ ውን : አቅርበው : ይሹሙት ። ነገር : ግን : በዘመን : የሚበልጠውን : መሾም : ሕግን : ለመፈጸም : ተስማሚ : አይደለም ። በዘመን :

ሥርዓት ፡ ኢኮነ ፡ ሥርዓተ ፤ ወለእመኒ ፡ ተሠይመ ፡ ዘይንእሶሙ ፡ በመዋዕል ፡ እምደለወ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘያፈደፍድ ፡ አእምሮ ፡ ወካልኡኒ ፡ ዘያሜኒ ፡ አመግቦተ ፡ ይረስይዎ ፡ ኖላዌ ፡ ለዘይፈቅዶ ፡ ፍትሐ ፡ ዝኩ ፡ ዘመን ።

፳፱ ወለእመ ፡ ኮነት ፡ መፍቅድ ፡ ኀበ ፡ ፍድፋዴ ፡ አእምሮ ፡ መጻሕፍት ፡ በምክንያተ ፡ አሰተርእዮተ ፡ ዕልወታት ፡ ይሚምዎ ፡ ለማእምረ ፡ መጻሕፍት ። ወለእመኒ ፡ ኮነት ፡ መፍቅድ ፡ ኀበ ፡ ሠናየ ፡ ምግብና ፡ ይሚምዎ ፡ ለዘይሜግብ ፡ በሠናይ ። ወእመሰ ፡ ኮነ ፡ ዕሩየ ፡ ተጋእዞቶሙ ፡ እምኵሉ ፡ ፍና ፡ ወተጋእዞ ፡ ከመ ፡ ይሚሙ ፡ ካልአኒሆሙ ፡ ይግባእ ፡ ግብሮሙ ፡ ኀበ ፡ ዕፃ ፡ በዲበ ፡ ታቦት ። ወይኄይስ ፡ ኅሮየተ ፡ ካልአኒሆሙ ፡ ለእመ ፡ ተረክበ ። እስመ ፡ ተጋእዞቶሙ ፡ በእንቲአሃ ፡ ያቈስሎሙ ። ወእኮ ፡ ረኪቦተ ፡ ትሩፈ ፡ ምግባር ፡ ዘይከልእ ፡ ለንኡሰ ፡ መዓርግ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ፍጹመ ፡ ለዐቂበ ፡ ሥርዓታት ። እስመ ፡ ፍድፋዴ ፡ ትሩፋት ፡ ትበጽሕ ፡ ውስተ ፡ ኅርየት ። ወእኮ ፡ ዘተዐዱ ፡ ውስተ ፡ ሥርዓታት ፡ ድልዋት ። ወለሰብእ ፡ ኅርየት ፡ ይደልዎሙ ፤ ከመ ፡ የሀብዋ ፡ ለዛቲ ፡ ሢመት ፡ ለዘድልው ፡ ላቲ ። ወእመሰ ፡ አበዩ ፡ ይከውኖሙ ፡ አበሳ ።

፴ ወኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ትኩን ፡ ዛቲ ፡ ሢመት ፡ ለ፪ቱ ፡ በ፩ዱ ፡ ዘመን ፤ ወበ፩ዱ ፡ መንበር ። ወእመሰ ፡ ኮነ ፡ ዝ ፡ በ፩ ፡ ሀገር ፡ ትጽናዕ ፡ ለዘተሠይመ ፡ ቅድመ ። ወለእመኒ ፡ ተውህበት ፡ ለእለ ፡ ይደልዎሙ ፡ ውስተ ፡ ፪ቱ ፡ አህጉር ፡ ትቁም ፡ ለዘተውህበት ፡ ሎቱ ፡ ቅድመ ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ ዘደለወት ፡ ቦቱ ፡ ልማድ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዝንቱ ፡ ውስተ ፡ ብሔር ፡ እሐቲ ፡ ትቁም ፡ ለዘተሠይመ ፡ ቅድመ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዝንቱ ፡ በ፩ ፡ ጊዜ ፡ ይደሉ ፡ ለለ፩ ፡ እምኔሆሙ ፡ ይግድፍ ፡ እምላዕለ ፡ ነፍሱ ፡ ወይደልዎሙ ፡ ለእለ ፡ የኀርዩ ፡ ከመ ፡ ይኅረይዎ ፡ ለዘተሠይመ ፡ ቀዳሚ ፡ እምኔሆሙ ፡ ባቲ ። ወለእመ ፡ ተዓረዩ ፡ ይኩን ፡ በዕፃ ፡ ዘታቦት ፡ ወይቁሙ ።

፴፩ ወለእመ ፡ አዘዘ ፡ በእንቲአሃ ፡ ተሠያሚሃ ፡ ለዘ ይሠየም ፡ እምድኅሬሁ ፡ እኮ ፡ ዘየአክል ፡ በእንቲአሃ ፡ ትእዛዘ ፡ ዚአሁ ። አላ ፡ ያቅድሞ ፡ ተኀርዮተ ፡ ዚአሁ ፡ ከመ ፡ ካልአኒሁ ። ወይኩን ፡



የሚያንሰው ፡ ቢሾም ፡ በተገባው ፡ ነበር ። ከነርሱ ፡ አንዱ ፡ አብዝቶ ፡ የተማረ ፡ ቢሆን ፡ ሁለተኛውም ፡ አስተዳዳሪነትን ፡ ዐዋቂ ፡ ቢሆን ፡ ጊዜ ፡ የሚፈቅደውን ፡ ይሾሙት ።

፳፱ ክህደቶች ፡ በመብዛታቸው ፡ ምክንያት ፡ መጻሕፍትን ፡ አብዝቶ ፡ የተማረው ፡ ቢፈለግ ፡ መጽሐፍ ፡ ዐዋቂውን ፡ ይሹሙት ። የተፈለገው ፡ መልካም ፡ አስተዳዳሪን ፡ ለማግኘት ፡ ቢሆን ፡ በበጎ ፡ አስተዳደር ፡ የሚያስተዳድረውን ፡ ይሹሙት ። በሁሉም ፡ መንገድ ፡ ክርክራቸው ፡ እኩል ፡ ቢሆን ፤ ወዳጆቻቸውንም ፡ ለመሾም ፡ ቢከራከሩ ፡ በታቦት ፡ ላይ ፡ ዕጣ ፡ ይጣሉ ። ቢያገኙስ ፡ ሌሎችን ፡ መምረጥ ፡ ይሻላል ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ መከራከራቸው ፡ ያቆስላቸዋልና ። በምግባር ፡ በትሩፋት ፡ ፍጹም ፡ የሆነውን ፡ ማግኘት ፤ ሥርዓቱን ፡ ለመፈጸም ፡ ፍጹም ፡ ከሆነ ፡ ዘንድ ፡ በማዕርግ ፡ ያነሰውን ፡ ከሹመት ፡ የሚከለክለው ፡ አይደለም ። ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ ለመመረጥ ፡ ታበቃለችና ። የተሠሩትን ፡ ሕጎች ፡ ግን ፡ የምታፈርስ ፡ አይደለችም ። መራጮች ፡ ይህችን ፡ ሹመት ፡ ለሚገባው ፡ ሰው ፡ መስጠት ፡ ይገባቸዋል ። ይህንንም ፡ ባያደርጉ ፡ ኃጢአት ፡ ይሆንባቸዋል ።

፴ ይህች ፡ ሹመት ፡ በ፩ ፡ ዘመንና ፡ በ፩ ፡ ሀገር ፡ ለሁለት ፡ ሰዎች ፡ ልትሆን ፡ አይገባም ። ይህ ፡ በአንድ ፡ ሀገር ፡ ከተደረገ ፡ ግን ፡ አስቀድሞ ፡ ለተሾመው ፡ ትጽና ። ለሚገባቸው ፡ ሰዎች ፡ በሁለት ፡ ሀገሮች ፡ ብትሰጥ ፡ ልማድ ፡ ተገቢ ፡ በሚያደርገው ፡ አገር ፡ አስቀድሞ ፡ ለተሾመው ፡ ትጽናለት ። ይህ ፡ በአንዲት ፡ ቦታ ፡ ቢሆን ፡ አስቀድሞ ፡ ለተሾመው ፡ ትጽና ። ይህ ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ ከነርሱ ፡ አንዱም ፡ አንዱ ፡ ሊተዋት ፡ ይገባል ። መራጮችም ፡ አስቀድሞ ፡ የተሾመውን ፡ መምረጥ ፡ ይገባቸዋል ። ተከራክረው ፡ ቢገኙ ፡ በታቦቱ ፡ ፊት ፡ ቁመው ፡ በዕጣ ፡ ይሁን ።

፴፩ ሹም ፡ የነበረው ፡ ከእርሱ ፡ ቀጥሎ ፡ ለሚሾመው ፡ ሰው ፡ ቢያዝ ፡ የእርሱ ፡ ትእዛዝ ፡ በቂ ፡ አይደለም ። እንደ ፡ ጓደኞቹ ፡ ይምረጡት ፡ እንጂ ። ይኸውም ፡ ነውር ፡ ከሌለበት ፡ ከት

ዝንቱ ፡ እምትጋሀ ፡ ሥራሒ ፡ ዘአልቦ ፡ ውስ
ቴቱ ፡ ነውር ።

፸፪ ወይደልዎሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ከመ ፡ ያእምሩ ፡ ተሠ
ያሚሃ ፡ በስሙ ፡ ወእርእያሁ ፡ ወግእዘ ። ወኢ
ደሉ ፡ ከመ ፡ ያጠይቆ ፡ በዓይኑ ፡ ወአስተሐም
ሞተ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘእንበለ ፡ በግብሩ ፡
እምበብእ ፡ ኀርየት ፡ ወይደልዎ ፡ ሎቱ ፡ ላዕለ
እዘዘ ፡ ግብራት ። ወኵሎሙ ፡ ይጠይቁ ፡ ኪያሁ፡
ግብረ ፡ ከዊኖቱ ፡ ሎቱ ። ወይድልዉ ፡ በመዳ
ልው ፡ ለእሙ ፡ ተረክቡ ፡ ኀቢሁ ፡ ፳ቱ ፡ ግብ
ራት ።

፸፫ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዐቂበ ፡ ሃይማኖት ፡ በከመ ፡
ተሠርዐ ፡ እመሠረቱ ፡ ወዘቆመ ፡ በአስተጋ
ብእ ፡ እምቃለ ፡ ሐዋርያት ፡ እምዝኒ ፡ ማኅበ
ራት ፡ ውኩፋት ፡ ወእምዝኒ ፡ ማኅበረ ፡ አበው ፡
እለ ፡ ተጋብኡ ፡ ለተወከፎተ ፡ ቃሎሙ ፡ በመ
ተረ ፡ ዕልወታቲሆሙ ፡ ለፍሉጣን ፡ እምሃይማ
ኖት ፡ ወሥዒረ ፡ ሀከክ ፡ በዘትከውን ፡ ሃይማ
ኖት ፡ ዕቅብተ ፡ እምዕቅፍት ፡ ወሕዝብኒ ፡ ይር
ከቡ ፡ ዳኅና ፡ እምነ ፡ ዳኅፃት ።

፸፬ ወዳግማዊ ፡ እውዕአተ ፡ ፍትሕ ፡ በጽድቅ ፡
ወመቲረ ፡ ጋእዛት ።

፸፭ ወሣልስ ፡ አብዝኆ ፡ ሀብት ፡ ለእለ ፡ ይደልዎሙ
ዘእንበለ ፡ አክብሮተ ፡ አሐዱ ፡ ወኢአሕጽጾት ፡
ወውሂቦቱሂ ፡ በአሐዱ ፡ ጊዜ ፡ እንዘ ፡ ኢያቀ
ድም ፡ ወኢያስተድኅር ።

፸፮ ወራብዕ ፡ ሠይመ ፡ ሢመታት ፡ ለእለ ፡ ይደል
ዎሙ ፡ ወአስተዳልዎ ፡ ንዋያት ፡ በእንተ ፡ ምጽ
ዋት ፡ ለኄራን ፡ ወለምእመናን ።

፸፯ ወኃምስ ፡ ከመ ፡ ይርአይ ፡ ግብራተ ፡ ኵሉ ፡
ወይድልዎን ፡ ለግብራት ፡ ድልዋት ፡ በነፍሱ ፡
ወይብል ፡ ይበቍዐኒ ፡ ዘአባሕክዎሙ ፡ ውስተ ፡
ኵሉ ፡ ምግባራት ፡ ወኢይፍጥር ፡ ካልአ ፡ በር
እሱ ፡ ረባሐ ፡ ኵሉ ፡ ግብራት ። ወኢይትገበር ፡
ግብረ ፡ ጣዕማት ፡ ወኢለገቢረ ፡ ቅንየት ፡ ሎቱ ፡
እስመ ፡ ቅንየትሰ ፡ ውእቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ባሕቲቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ጊዜ ፡ ውሉን ። ወይደልዎ ፡
ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይትማከሮሙ ፡ ለሰብእ ፡ አእ



ጋቱ ፡ የተነሣ ፡ ይሁን ።

፸፪ ሕዝቡም ፡ የሚሾመውን ሰው ፡ በስሙና ፡ በመ
ልኩ ፡ በጠባዩም ፡ ሊያውቁት ፡ ይገባል ። ከመ
ራጮች ፡ ወገን ፡ በሥራው ፡ እንጂ ፡ በዓይኑ ፡
አንዱ ፡ እንኳ ፡ ጠቅሶ ፡ ሊያሳየው ፡ አይገባ
ውም ። እርሱም ፡ በሥርዓት ፡ ጸንቶ ፡ መኖር ፡
ይገባዋል ። ሁሉም ፡ ለእርሱ ፡ የሚገባውን ፡
እርሱን ፡ ይጠይቁ ። አምስቱ ፡ ግብራት ፡ በእ
ርሱ ፡ ዘንድ ፡ ይገኙ ፡ እንደሆነም ፡ ይመዝኑ ፡
ይመርምሩ ።

፸፫ ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ በመጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ተጻ
ፈው ፡ ሃይማኖትን ፡ መጠበቅና ፡ ከሐዋርያት ፡
ቃል ፡ በመሰብሰብ ፡ የጸና ፡ መሆን ፡ ነው ።
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሊቀበሏቸው ፡ የተገባ ፡ ማኅ
በሮችን ፡ መቀበል ፡ ነው ። ከዚህም ፡ ቀጥሎ ፡
ከሃይማኖት ፡ የተለዩትን ፡ ከሀደቶች ፡ በመለ
የት ፡ ቃላቸውን ፡ ለመቀበል ፡ የተሰበሰቡትን ፡
የአበውን ፡ ማኅበር ፡ መቀበል ፡ ነው ። ሃይማ
ኖት ፡ ከጥርጥር ፡ የተጠበቀች ፡ በምትሆን ፡
ገንዘብ ፡ ጠብ ፡ ክርክርን ፡ ለማራቅ ፡ ሕዝቡም ፡
ከመሰነካከል ፡ ድኅነትን ፡ እንዲያገኙ ፡ ለማድ
ረግ ፡ የተሰበሰቡትን ።

፸፬ ሁለተኛው ፡ ፍርድን ፡ በእውነት ፡ መስጠትና ፡
ጠብ ፡ ክርክርን ፡ ማራቅ ፡ ነው ።

፸፭ ሦስተኛው ፡ ለሚገባቸው ፡ ሰዎች ፡ ለአንዱ ፡
ሳያበልጥ ፡ ለአንዱ ፡ ሳያሳንስ ፡ ሀብትን ፡ (ስጦ
ታን) ፡ አብዝቶ ፡ መስጠት ፡ ነው ። እሰጣጡም፡
ሳያዘገይና ፡ ሳያስቀድም ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡
ይሁን ።

፸፮ አራተኛው ፡ የሚገባቸውን ፡ ሰዎች ፡ መሾም ፡
ነው ። ለደኆችና ፡ ለምእመናንም ፡ ስለ ፡ ምጽ
ዋት ፡ ገንዘብ ፡ መሰብሰብ ፡ ነው ።

፸፯ አምስተኛውም ፡ የሁሉን ፡ ሥራ ፡ ይመረምር ፡
ዘንድ ፡ ነው ። የሚገቡትን ፡ ሥራዎች ፡ እርሱ ፡
ራሱ ፡ ይመርምር ። በሥራው ፡ ሁሉ ፡ ያሠለጠ
ንኋቸው ፡ ይበቃኛል ፡ እይበል ። ለራሱ ፡
ጥሪት ፡ አያብጅ ፡ የላመ ፡ የጣመ ፡ ለመቅመስ ፡
ታዘዙኝ ፡ ለማለትም ፡ እይድከም ። ጊዜ ፡ ሳይ
ወስኑ ፡ መገዛት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡
ነውና ። የእውቀት ፡ ሰዎችን ፡ ስለ ፡ ፍርድና ፡
ስለ ፡ ቅጣት ፡ ሊያማክራቸው ፡ ይገባዋል ።

ምሮ ፡ በእንተ ፡ ሠናኔ ፡ ወፍትሕ ፡ ወሰስብእ ፡ ምክርኒ ፡ በእንተ ፡ ምክር ፡ ዘእንበለ ፡ ንሚት ፡ ወእፍልሶ ፡ ወዘእንበለ ፡ እሲር ፡ ወፈቲሕ ። ወለእመ ፡ እንጎ ፡ ቀዊመ ፡ ዘዘይደልዎ ፡ ወያዘ ልፍ ፡ ምሂረ ፡ ትእዛዛት ፡ ይደልዎሙ ፡ ተአዝ ዞቶ፡ ወእዕብዮቶ፡ ወአከብሮቶ፡ ወአጽድቆተ፡ ቃሎ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዕንቡዘ ፡ ልቡናሁ ፡ ወኮኑ ፡ ይሴፈዉ ፡ ተፈውሶቶ ፡ ይጽንሕዎ ። ወእመሰ ፡ ኢይሴፈዉ ፡ ወኮነ ፡ ዘመነ ፡ ሕማሙ፡ ጎዳጠ ፡ ጥቀ ፡ ኢይክልእዎ ፡ እምአዝልፎተ ፡ ሢመት ፡ ሎቱ ። ወለእመሰ ፡ በዝጎ ፡ እምዘመነ፡ ተፈውሶ ፡ ይክልእዎ ።

፳፰ ወእኮ ፡ ሡሉ ፡ ዘይትከላእ ፡ እምእኂዘ ፡ ሢመት ፡ በእንተ ፡ ደዌ ፡ ኅላፊ ፡ ለእመ ፡ ይረክብ ፡ በድ ኅሬሁ ፡ ጥዒና ። እስመ ፡ እኂዘ ፡ ሢመት ፡ ትቁም ፡ ሎቱ ፡ እስከ ፡ የኀሥሥ ፡ ሎቱ ፡ ዳኅና ፡ ፍጽምተ ፡ ወለፀእትስ ፡ እምሢመት ፡ ይትረ ከብ ፡ ውስቴቱ ፡ ሕጸት ፡ ፍጹም ፡ ወሶበሂ ፡ ተሞ ቅሐ ፡ በሐብለ ፡ ደዌ ፡ ወዘይመስሎ ፡ ለዝንቱ ፡ ድልው ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይጽንሕዎ ፡ በእንተ ፡ ዘይሴፎ ፡ ድኂነ ። ወእመሰ ፡ ኖኀ ፡ ዘመነ ፡ ደዌሁ ፡ መፍትው ፡ ለሰብእ ፡ ኅርየት ፡ ከመ ፡ ይሚሙ ፡ ህየንቴሁ ፡ ካልእ ፡ ዘይተልዎ ። ወለ እመኒ ፡ ይትፌወስ ፡ ድኅረ ፡ መፍትው ፡ ውእቱ፡ ከመ ፡ ይሠየም ፡ ህየንቴሁ ፡ ሕያው ፡ በመባ ሕተ ፡ ድዉይ ፡ እስከ ፡ ይትፌወስ ፡ ወይገብእ ፡ ኀበ ፡ መንበሩ ። ወለእመሰ ፡ ተዐውቀ ፡ ከመ ፡ ይመውት ፡ ወኢይትፌወስ ፡ መፍትው ፡ ይሠ የም ፡ ካልእ ፡ በከመ ፡ ነገርነ ፡ ቀዳሚ ።

፳፱ ወፈጽሞተ ፡ ነገር ፡ በእንተ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወሥርዓተ ፡ ሢመቱ ፡ ወዘይመስሎ ፡ ለዝንቱ ፡ ተነግረ ፡ በቀኖናት ፡ ከመ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወኢ ይሠየሙ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ዘብሔረ ፡ መንበሩ ፡ እንበለ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በዓለ ፡ መንበር ፡ ዘእስ ክንድርያ ።

የምክር ፡ ሰዎችንም ፡ ያለ ፡ ማፍረስና ፡ ያለ ፡ ማፍለስ ፡ ያለ ፡ ማስርና ፡ ያለመፍታት ፡ ሊያማ ክራቸው ፡ ይገባዋል ። በሚገባው ፡ ጸንቶ ፡ ቢኖር ፡ ሕጋጋትንም ፡ ማስተማር ፡ ቢያዘወትር ፡ ሊታዘዙለትና ፡ ፈጽሞ ፡ ሊያከብሩት ፡ ቃሉንም፡ ሊቀበሉት ፡ ይገባቸዋል ። አእምሮውን ፡ ያጣ ፡ ቢሆንም ፡ ይድናል ፡ ብለው ፡ ተስፋ ፡ የሚያደ ርጉት ፡ ከሆነ ፡ ይጠብቁት ። ይድናል ፡ ብለው ፡ ተስፋ ፡ ባያደርጉ ፡ ግን ፡ የታመመበትም ፡ ዘመን ፡ በጣም ፡ ጥቂት ፡ ቢሆን ፡ ከሹመት ፡ አይሻሩት ። ከመዳን ፡ ቢዘገይ ፡ ግን ፡ ይሻሩት ።

፳፰ በኋላ ፡ የሚድን ፡ ከሆነ ፡ በሚያልፍ ፡ በሽታ ፡ ምክንያት ፡ ሹመትን ፡ ከመያዝ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚከለከል ፡ አይደለም ። ፍጹም ፡ ድኅነትን ፡ እስኪያገኝ ፡ ድረስ ፡ ልትጸናለት ፡ ይገባልና ። ከሹመት ፡ መሻር ፡ ግን ፡ ፍጹም ፡ ጉድለት ፡ ይገኝበታል ። በደዌ ፡ ገመድና ፡ በሚመስለው ም ፡ ቢያዝ ፤ ድኅነትን ፡ ተስፋ ፡ ስለሚያደርግ ፡ ሊጠብቁት ፡ ይገባል ። የበሽታው ፡ ዘመን ፡ ቢበዛ ፡ መራጮች ፣ በእርሱ ፡ ፈንታ ፡ ሌላውን ፡ ሊሾሙ ፡ ይገባቸዋል ። በኋላም ፡ ቢድን ፡ እስኪ ድንና ፡ ወደ ፡ መንበሩ ፡ እስኪመለስ ፡ ድረስ ፡ ጤነኛው ፡ ሰው ፡ በበሽተኛው ፡ ፈቃድ ፡ ስለእ ርሱ ፡ ሆኖ ፡ ሊሾም ፡ ይገባዋል ። እንደማይድ ንና ፡ እንደሚሞት ፡ ቢታወቅ ፡ ግን ፡ አስቀድ መን ፡ እንደ ፡ ተናገርን ፡ ሌላው ፡ ሊሾም ፡ ይገ ባዋል ።

፳፱ ስለ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ የነገሩ ፡ መጨረሻ ፡ የሹ መቱም ፡ ሥርዓት ፡ ይህን ፡ የሚመስለውም ፤ ለሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ የሚገባው ፡ በመጻሕፍት ፡ ተነገረ ። ያለ ፡ እስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ፈቃድ ፡ በሀገረ ፡ መንበሩ ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ኤጲስ ቆጳሳት ፡ አይሾሙ ።

## አንቀጽ ፡ ኃምስ ።

### በእንተ ፡ ኤጲስቆጳሳት ።

፩ ኤጲስቆጳስስ ፡ ከመ ፡ ኖላዊ ፡ በከመ ፡ ተነግረ ፡ በዲድስቅልያ ። ወርእየቱ ፡ ወሀላዌሁ ፡ ይኩን ፡ በ፫ ፡ ገጻት ፡ ቀዳማዊ ፡ እምቅድመ ፡ ኅርየቱ ፡ ወሢመቱ ፡ ወዳግም ፡ ግብረ ፡ ኅርየቱ ፡ ወሣ

## አንቀጽ ፡ ፭ ።

### ስለ ፡ ኤጲስቆጳሳት ።

፩ ኤጲስቆጳስስ ፡ በዲድስቅልያ ፡ እንደ ፡ ተነገረ ፡ እንደ ፡ ጠባቂ ፡ ነው ። አስተያየቱና ፡ አኗኗሩ ፡ በ፫ ፡ ወገን ፡ ይሁን ። መጀመሪያው ፡ ከመመረ ጡና ፡ ከመሾሙ ፡ በፊት ፤ ሁለተኛው ፡ የአመ

ልስ ፤ እምድኅረ ፡ ሢመቱ ፡ ፍጽምት ።

፻፩ ቀዳማዊትሰ ፡ ትትከፈል ፡ ኀበ ፡ ፫ ፡ አከፋል ፡ አሐቲ ፡ እምኔሆን ፡ እንተ ፡ ታጤይቅ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ድልው ፡ ለኤጲስቆጶስና ፡ ወካልእ ታሂ ፡ ምክንያት ፡ እንተ ፡ ትከልእ ፡ ሎቱ ፡ እምኔሃ ፡ ወሣልሰታ ፡ በዘኢይደልዎ ፡ ወኢይከ ልእዎ ፡ አላ ፡ ኤጲስቆጶስና ፡ ምስሌሃ ፡ ድልው ፡ ሎቱ ።

፻፪ ወድልወትሰ ፡ ፰ቱ ፡ ይእቲ ፤ ቀዳሚት ፡ ወዳግ ሚት ፡ ወሣልሲት ፡ ወራብዒት ፡ በእንተ ፡ ሑረቱ ፡ ወግዕዙ፡ ወሕይወቱ ፡ ወተኃርዮቱ ።

፻፫ ይቤ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ጤት ፡ ዘ፩ቱ ፤ "ወአ ሙን ፡ ውእቱ ፡ ነገሩ ፡ እስመ ፡ ለእመ ፡ አፍ ቀረ ፡ ፩ዱ ፡ ከመ ፡ ይሠየም ፡ ኤጲስቆጶስና ፤ ነዋ ፡ አፍቀረ ፡ ግብረ ፡ ሠናየ ። ወነዋ ፡ ይደሉ ፤ ይኩን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘኢተረከበ ፡ ውስቴቱ ፡ ነውር ። ወዘአውሰበ ፡ አሐተ ፡ ብእሲተ ፡ ዘን ቁሀ ፡ በኀሊናሁ ፡ ውእቱ ፡ ጠቢብ ፡ ወመናዝዝ ፡ ወመፍቀሬ ፡ ነግድ ፡ መምህር ፡ ዘኢያበዝኅ ፡ ስትየ ፡ ወይን ፡ ወዘኢያፈጥን ፡ እዴሁ ፡ ለዘቢጥ። አላ ፡ ይኩን ፡ ትሑተ ፡ ወኢይኩን ፡ ተጋእዜ ፡ ወኢመፍቀሬ ፡ ንዋይ ፡ ወዘያሤኒ ፡ ሠሪዐ ፡ ቤቱ፡ ወሕፃንተ ፡ ደቂቁ ፡ ወዘያኔብሮሙ ፡ ኀበ ፡ ተአ ዝዞት ፡ ወኵሉ ፡ ንጽሕ ። እመሰ ፡ ውእቱ ፡ ዘኢ ያሤኒ ፡ ሠሪዐ ፡ ቤቱ ፡ እፎ ፡ ያሤኒ ፡ ሠሪዐ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወቤተ ፡ ክርስቲያን ። ወኢይኩን ፡ ተክለ ፡ ሐዲሰ ፡ ከመ ፡ ኢይዘኀር ። ወኢይደቅ ፡ ውስተ ፡ ሥቃየ ፡ ሰይጣን" ፡ ወይ ደሉ ፡ ካዕበ ፡ ከመ ፡ ይኩንዎ ፡ ሎቱ ፡ ስማዕተ ፡ በሠናይ ፡ እምዐላውያን ፡ ዚአነ ፡ በሃይማኖት ፡ ከመ ፡ ኢይደቅ ፡ ውስተ ፡ ትዕይርት ፡ ወውስተ ፡ አሕባለ ፡ ሰይጣን ።

፻፬ ድስቅ ፡ ፩ቱ ፡ ወከመዝ ፡ ሰማዕናሁ ፡ ለእግዚ እነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ይደልዎ ፡ ለኖላዊ ፡ ዘይሠይምዎ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ዘውስተ ፡ ኵሉ ፡ መካን ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ዘእንበለ ፡ ሒስ ፡ ወኢኄ



ራረጡ ፡ ሥራ ፡ ሦስተኛውም ፡ ፈጽሞ ፡ ከተ ሾመ ፡ በኋላ ፡ ያለው ፡ ነው ።

፻፩ መጀመሪያዪቱ ፡ በሦስት ፡ ክፍሎች ፡ ትከፈላ ለች ። ከነርሱ ፡ አንዲቱ ፡ ለኤጲስቆጶስነት ፡ የበቃ ፡ መሆኑን ፡ የምታስረዳ ፡ ናት ። ሁለተ ኛዪቱም ፡ እርሱን ፡ ከእርስዋ ፡ (ከሹመት) ፡ የምትከለክል ፡ ምክንያት ፡ ናት ። ሦስተኛ ዋም ፡ የማይገባውንና ፡ የማይከለክልበትን ፡ ታስረዳለች ፡ ከርስዋ ፡ ጋር ፡ ኤጲስቆጶስነት ፡ ይገባዋል ፡ እንጂ ።

፻፪ ለሹመት ፡ የሚበቃባቸው ፡ ሥራዎች ፡ ፬ ፡ ናቸው ። አንደኛዋና ፡ ሁለተኛዋ ፡ ሦስተኛዋ ፡ አራተኛዋ ፡ ስለ ፡ አኗኗሩና ፡ ስለ ፡ ጠባዩ ፡ ስለ ፡ ሕይወቱና ፡ ስለ ፡ አመራረጡ ፡ ትናገራ ለች ።

፻፫ ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ ጤት ፡ ፩ ፡ (፩ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፩-፯) ። እንዲህ ፡ አለ ። አንድ ፡ ሰው ፡ ኤጲስቆ ጶስነትን ፡ ሊሾም ፡ ቢወድ ፡ እነሆ ፡ መልካም ፡ ሥራን ፡ ወደደ ። ነውር ፡ የሌለበት ፡ ሰው ፡ ኤጲ ስቆጶስ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ። አንዲት ፡ ሴት ፡ ያገባ ፡ በሐሳቡ ፡ ንቁ ፡ የሆነ ፡ አዋቂ ፡ የሚያረጋጋ ፡ እንግዳ ፡ ተቀባይ ፡ መጠጥ ፡ የማ ያበዛ ፡ መምህር ፡ ይሁን ። ትሑት ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ለመማታት ፡ እጁን ፡ የማያፋጥን ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ። ተከራካሪና ፡ ገንዘብ ፡ ወዳጅ ፡ አይሁን ። ቤተ ፡ ሰቡን ፡ የሚያስተዳ ድርና ፡ ልጆቹን ፡ በሚገባ ፡ የሚያሳድግ ፤ ወደ ፡ መታዘዝና ፡ ወደ ፡ ንጽሕና ፡ የሚያደርሳቸውም፡ ይሁን ። እርሱ ፡ ቤተ ፡ ሰቡን ፡ በሚገባ ፡ የማያ ስተዳድር ፡ ከሆነ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤትና ፡ የክርስቲያንን ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ እንዴት ፡ ያስተዳ ድራል ? ። ሐዲስ ፡ ተክል ፡ በሃይማኖት ፡ አይ ሁን ። እንዳይታበይ ፤ በሰይጣን ፡ ፈተናም ፡ እንዳይወድቅ ። ዳግመኛም ፡ በሃይማኖት ፡ ከኛ ፡ ውጭ ፡ የሆኑት ፡ ሰዎች ፡ በመልካም ፡ ሥራው ፡ የመሰከሩለት ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ። በትዕቢ ትና ፡ በሰይጣን ፡ አሽክላ ፡ እንዳይወድቅ ።

፻፬ ድስቅ ፡ ፩ ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እን ዲህ ፡ ብሎ ፡ ሲናገር ፡ ሰማነው ፤ በየቦታው ፡ ላሉ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሆኖ ፡ የሚሾመው ፡ ጠባቂ ፡ ያለ ፡ ነውርና ፡ ያለ፡ በደል ፡ ይሁን ። ከሰው ፡ ሁሉ ፡ በደል ፡ የነጻ ፤

ጋይ ። ወይኩን ፡ ንጹሐ ፡ እምኵሉ ፡ ዓመፃ ፡ ዘስ
ብእ ፡ ወዘኢኮነ ፡ ሕይወቱ ፡ ሕጹጸ ፡ እምሂ ፡
ዓም ። ወለእመ ፡ ተከሀሎ ፡ ለይኩን ፡ ምሉእ ፡
እምኵሉ ፡ ትምህርት ፡ ወተማሃሰ ፡ ወማእምረ ፡
ነገር ፡ በቃሉ ።

፹፰ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ መንበሩ ፡ ንእሰ ፡ ወኢረከቡ ፡ ዘብዙኀ ፡ ዓመቲ ፡ ዐቢየ ፡ ልሀቅናሁ ፡ አላ ፡ ረከቡ ፡ ሕጹጸ ፡ በዓመት ፡ ልህቅናሁ ፡ ዘይከውኑ ፡ ሎቱ ፡ ስምዐ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ምስሌሁ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ድልው ፡ ለኤጲስቆጶስና ፡ ወከመ ፡ ውእቱ ፡ ነዋ ፡ አርአየ ፡ በውርዝዉናሁ ፡ ግብረ ፡ እእሩግ ፡ በፍሥሐ ፡ ወበሥርዓት ፡ ወጥበብ ፡ ወለዝንቱኒ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይፍትንዎ ፡ ወለእመ ፡ ተረከበ ፡ በከመ ፡ ኮንዎ ፡ ለምዐ ፡ ይሢምዎ ፡ በሰላም ።

፹፱ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ንእሰ ፡ እው ፡ ዐቢየ ፡ ወይኩን ፡ ፍሡሐ ፡ ወትሑተ ፡ ወሀዱአ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቤ ፡ በአፈ ፡ ኢሳይያስ ፡ ነቢይ ፡ ኀበ ፡ መኑ ፡ እኔጽር ፡ ዘእንበለ ፡ ኀበ ፡ ትሑታን ፡ ወየዋሃን ፡ እለ ፡ ይርዕዱ ፡ እምቃልየ ፡ ዘኵሉ ፡ ዘመን ። ወከማሁ ፡ ይቤ ፡ በወንጌልኒ ፡ ካዕበ ፡ በ፭ ፡ ምዕራፍ ፡ ብፁዓን ፡ የዋሃን ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ይወርስዋ ፡ ለምድር ። ወይኩን ፡ መሐሬ ፡ እስመ ፡ ይቤ ፡ ብፁዓን ፡ መሐርያን ፡ እስመ ፡ ሎሙኒ ፡ ይምሕርዎሙ ። ወይኩን ፡ በዓለ ፡ ሰላም ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይቤ ፡ ብፁዓን ፡ ገባርያን ፡ ሰላም ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ውሉደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሰመዩ ። ወለትኩን ፡ ሕሊናሁ ፡ ሠናይተ ፡ ወንጽሕተ ፡ እምኵሉ ፡ እከይ ፡ ወዐመፃ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይቤ ፡ ብፁዓን ፡ ንጹሓን ፡ ልብ ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ይሬእይዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።

፺ ወይኩን ፡ ተዓጋሤ ፡ ቀዋሜ ፡ በኵሉ ፡ ሥርዓት ፡ ሠናይ ፡ ኢይኩን ፡ ተሃዋኬ ፡ ወኢሰካሬ ፡ ወኢቍጡዐ ፡ ወኢመፍቀሬ ፡ ንዋይ ፡ ወወርቅ ፡ ወይፍትንዎ ፡ ካዕበ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ዘአልቦቱ ፡ ነውር ፡ በኵሉ ፡ እምሳል ፡ ዘዝንቱ ፡ ዓለም ። እስመ ፡ ጽሑፍ ፡ ውእቱ ፡ ዘይብል ፡ ይፍትንዎ ፡ ለዘያነብርዎ ፡ በዝየ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ዘእንበለ ፡ ነውር ። ወኢይኩን ፡ መዓትመ ፡ እስመ ፡ ትብል ፡ ጥበብ ፡ እስመ ፡ መዓት ፡ ታማስን ፡ ጠቢባን ። ወይኩን ፡ መፍቀሬ ፡ ሰብእ ፡ እስመ ፡ ይብል ፡

ዕድሜውም ፡ ከ፶ ፡ ዓመት ፡ ያላነሰ ፡ ይሁን ። ቢቻለውስ ፡ ትምህርትን ፡ ሁሉና ፡ ምክርን ፡ የተመላ ፡ በቃሉ ፡ ነገር ፡ አዋቂም ፡ ይሁን ።

፹፰ ሀገረ ፡ ስብከቱ ፡ ታናሽ ፡ ቢሆን ፡ በዕድሜውም ፡ ሽማግሌ ፡ የሆነ ፡ ባያገኙ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ለኤጲስቆጶስነት ፡ እንደሚበቃ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ የሚኖሩት ፡ ሰዎች ፡ የመሰከሩለት ፡ ወጣት ፡ ቢያገኙ ፡ በጉልምስናውም ፡ ወራት ፡ የሽማግሌዎችን ፡ ሥራ ፡ በደስታና ፡ በሥርዓት ፡ በዘዴ ፡ እንዳሳየ ፡ ቢመሰክሩለት ፡ ይህንን ፡ ሊፈትኑት ፡ ይገባል ። እንደ ፡ መሰከሩለት ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝ ፡ ተስማምተው ፡ ይሹሙት ።

፹፱ ትንሽ ፡ ወይም ፡ ትልቅ ፡ ቢሆን ፡ ደስተኛና ፡ ትሑት ፡ ጸጥተኛም ፡ ይሁን ። እግዚአብሔር ፡ በነቢዩ ፡ በኢሳይያስ ፡ አፍ ፡ (ኢሳ ፡ ፷፮ ፡ ፪-፱) ። ወደ ፡ ማን ፡ እመለከታለሁ ። ከቃሌ ፡ የተነሣ ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ ወደሚፈሩና ፡ ወደሚንቀጠቀጡ ፡ የዋሃንና ፡ ትሑታን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ብሏልና ። እንዲሁም ፡ በወንጌል ፡ (ማቴ ፡ ፭ ፡ ፮-፱) ። በ፭ኛው ፡ ምዕራፍ ፡ እንዲህ ፡ ተብሏል ። የዋሃን ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ እነርሱ ፡ ምድርን ፡ ይወርሳሉና ። የሚራራም ፡ ይሁን ፡ የሚራሩ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ ለነርሱም ፡ ይራሩላቸዋል ፡ ብሏልና ። ሰላማዊ ፡ ይሁን ፡ ሰላምን ፡ የሚያደርጉ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ እነርሱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ይባላሉ ፡ ብሏልና ። ሐሳቡም ፡ ያማረች ፡ የጸራች ፡ ከክፋትና ፡ ከዐመፅ ፡ ሁሉ ፡ የነጻች ፡ ትሁን ። ልባቸው ፡ ንጹሕ ፡ የሆነላቸው ፡ ሰዎች ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ እነርሱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያዩታል ፡ ብሏልና ።

፺ የሚታገሥና ፡ በመልካም ፡ ሥርዓት ፡ ሁሉ ፡ የጸና ፡ ይሁን ። የሚታወክና ፡ የሚሰክር ፡ ቁጡ ፡ ገንዘብ ፡ ወዳጅ ፡ አይሁን ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ነውር ፡ የሌለበት ፡ መሆን ፡ አለመሆኑን ፡ ዳግመኛ ፡ ይፈትኑት ። "በዚህ ፡ የሚያስቀምጡትን ፡ ይፈትኑት ፡ ነውር ፡ የሌለበት ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡" (፩ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፲) ። የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ አለና ። ቁጡ ፡ አይሁን ፡ ጥበብ ፡ "ቍጣ ፡ አዋቂዎችን ፡ ታጠፋለች ፡ ትላለችና ፡" (ምሳ ፡ ፲፭ ፡ ፩) ። ሰውን ፡ አፍቃሪ

ለማዘዝኒ ፡ በዝንቱ ፡ የአምርክሙ ፡ ኮሎ ፡ ከመ ፡ አርዳእየ ፡ አንትሙ ፡ ለእመ ፡ ተፋቀርክሙ ፡ በበይናቲክሙ ።

፴፰ ጠስ ፡ ፳ወ፰ ፡ ወበእንተ ፡ እለ ፡ ይኀርዩ ፡ ኪያሁ ፡ ይደሉ ፡ ይኩን ፡ ኮሎ ፡ ለለ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘተበደወ ፡ ፴ ፡ ዓመተ ።

፴፱ ኃምስ ፡ ወይኩን ፡ መነኮስ ፡ እምእለ ፡ ቦሙ ፡ መዓርግ ፡ ዘምሥዋዕ ፡ አው ፡ እምዘ ፡ ይከውን ፡ ስሑተ ፡ ሥርዓተ ፡ ውዳሴ ፡ ወኢይቴኔ ፡ ይሠየም ፡ ሕዝባዊ ፡ ዘእንበለ ፡ እምድኅረ ፡ ዐጸባ ፡ ወእምድኅረ ፡ አቀመ ፡ ላዕለ ፡ ነፍሱ ፡ ዐቀበ ፡ ቀኖናት ፡ ቅዱሳት ። ወዝንቱኒ ፡ በከመ ፡ ተነግረ ፡ ውስተ ፡ ቀኖናተ ፡ አትናቴዎስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘቍስጥንጥንያ ፡ ወውእቱ ፡ ዘንበር ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ መነኮስ ፡ አው ፡ ካህነ ።

፵ ሳድስ ፡ ይኩን ፡ በሥምረተ ፡ ሕዝብ ፡ ዘይሠየም ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ወበሥምረተ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሰኒ ፡ ድስቅ ፡ ፻ወ፯ ፡ ለይሠየም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በኅሪየተ ፡ ኮሎሙ ፡ ሕዝብ ፡ ኪያሁ ፡ በከመ ፡ ሥምረተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ።

፵፩ ዘኒቅያ ፡ ፱ ፡ ወስእመ ፡ ኀሠሠ ፡ አሐዱሂ ፡ ኤጲስቆጶስና ፡ ወሠምሩ ፡ ቦቱ ፡ ኮሎሙ ፡ ሰብአ ፡ ሀገሩ ፡ ወኢሠምረ ፡ ቦቱ ፡ ጳጳስ ፡ ብሔሩ ፡ ኢይደልዎ ፡ ኤጲስቆጶስና ፡ ዘእንበለ ፡ በትእዛዘ ፡ ዚአሁ ። ወዘንተ ፡ ለእመ ፡ ተበደወ ፡ ሲኖዶስ ፡ ያወግዞ ፡ ወይትኀደግ ፡ ኤጲስቆጶስናሁ ። ወለእመሰ ፡ ኀብሩ ፡ በእንቲአሁ ፡ ዘይበዝኁ ፡ ወሠምሩ ፡ ቦቱ ፡ ጳጳስ ፡ ወሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ይግበሩ ፡ በምክሮሙ ፡ ለእለ ፡ ይበዝኁ ።

፵፪ ረስጠጅ ፡ ፩ ፡ ይሠየም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በሥምረተ ፡ ጳጳሱ ፡ ወሰብአ ፡ ብሔሩ ፡ ወየሀልዉ ፡ ከመ ፡ ይሢሞዎ ፡ ፪ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ አው ፡ ፫ ፡ ረስጠጅ ፡ ፪ ፡ ቀሲስስ ፡ ወዲያቆን ፡ ወዘይቴሐቶሙ ፡ ይሠየሙ ፡ እም፩ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወይሳተፎሙ ፡ ወይባርኮሙ ፡ ፩ ፡ ኤጲስቆጶስ ።

፵፫ ሰብዕ ፡ ነበረ ፡ ውስተ ፡ ቀኖናት ፡ ዘነገሥት ። መ፮ ፡ ወኢይሠየም ፡ ኤጲስቆጶስና ፡ ፍጡነ ፡ ዘእንበለ ፡ ተኀርዮቱ ፡ በእንተ ፡ ሃይማኖቱ ፡ ወእእምሮቱ ፡ ወሐሪቱ ፡ ወሥነ ፡ ዜና ፡ በእንቲ



ይሁን ፡ ጌታችን ፡ "እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ብትፋቀሩ ፡ በዚህ ፡ የኔ ፡ ደቀመዛሙርት ፡ እንደሆናችሁ ፡ ሁሉ ፡ ያውቃችኋል" ። (ዮሐ ፡ ፲፫ ፡ ፴፭ ።) ብሏልና ።

፴፰ ጠስ ፡ ፳፰ ። የሚመረጡት ፡ ሰው ፡ እያንዳንዱ ፡ ከሠላሳ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ።

፴፱ አምስተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ክህነት ፡ ካላቸው ፡ ከመነኮሳት ፡ ወይም ፡ የሚያስመሰግን ፡ ሥራ ፡ ካለው ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ መነኮሴ ፡ ይሁን ። ሕዝባዊ ፡ ግን ፡ በችግር ፡ ጊዜ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ቅዱሳት ፡ ሕጎችንም ፡ ካልፈጸመ ፡ በቀር ፡ ሊሾም ፡ አይገባም ። ይኸውም ፡ በቍስጥንጥንያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በአትናቴዎስ ፡ ሕጎች ፡ እንደ ፡ ተነገረው ፡ ነው ። ይኸውም ፡ መነኮሴ ፡ ወይም ፡ ካህን ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ እንደተጻፈው ፡ ነው ።

፵ ስድስተኛ ። በሚሾምባቸው ፡ ሕዝቦችና ፡ በሊቀ ፡ ጳጳሱም ፡ ፈቃድ ፡ ይሁን ። ድስቅ ፡ ፻፯ ። ኤጲስቆጶስ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፈቃድ ፡ በሕዝብ ፡ ምርጫ ፡ ይሾም ።

፵፩ ኒቅያ ፡ ፱ ። አንድ ፡ ሰው ፡ ኤጲስቆጶስነትን ፡ ሊሾም ፡ ቢፈልግ ፡ ሕዝቡም ፡ ቢስማሙ ፡ ያገሩ ፡ ጳጳስ ፡ ግን ፡ ባይፈቅድ ፡ ያለእርሱ ፡ ፈቃድ ፡ ኤጲስቆጶስነት ፡ መሾም ፡ አይገባውም ። ይህን ፡ ቢያፈርስ ፡ ሲኖዶስ ፡ ያወግዘዋል ። ኤጲስቆጶስነቱም ፡ ይቀራል ። ስለርሱ ፡ የሚበዙት ፡ ቢስማሙ ፡ ግን ፡ ጳጳሱና ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሱም ፡ ቢስማሙበት ፡ በድምፅ ፡ ብልጫ ፡ ይሹሙት ።

፵፪ ረስጠጅ ፡ ፩ ። ኤጲስቆጶስ ፡ በጳጳሱና ፡ በአገሩ ፡ ሰዎች ፡ ፈቃድ ፡ ይሾም ። ይሾሙት ፡ ዘንድ ፡ ፪ት ፡ ወይም ፡ ፫ት ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ይኑሩ ። ረስጠጅ ፡ ፪ ። ቄስና ፡ ዲያቆን ፡ ከዚያም ፡ በታች ፡ ያሉት ፡ ከአንድ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ይሾሙ ። አንድ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ባርኮ ፡ ይሹማቸው ፡ በሥራም ፡ ይተባበራቸው ።

፵፫ ሰባተኛ ። በነገሥታት ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ይገኛል ። መ፮ ። ስለ ፡ ሃይማኖቱና ፡ ስለ ፡ እውቀቱ ፡ ስለ ፡ አኗኗሩ ፡ ስለ ፡ መልካም ፡ ምግባሩም ፡ ሳይመረጥ ፡ ኤጲስቆጶስነትን ፡ ፈጥኖ ፡ አይሾም ። በየ

አሁ ፡ ወያስተፋልስዎ ፡ ውስተ ፡ መዓርገ ፡ ክህ ነት ፡ በመዓርግ ፡ እምድኅረ ፡ መዓርግ ፡ በበመ ዓርጉ ። ወለእመ ፡ ቆመ ፡ በሐሪት ፡ በኮሱ ፡ መዓ ርገ ፡ ድልወተ ፡ ሶቤሃ ፡ ይሠየም ።

፺፩ ሳምን ፡ ከመ ፡ ይትኅረይ ፡ እምብዙኃን ። በስ ፡ ፹ወ፯ ፡ ወኢይሠየም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘእንበለ ፡ ይንሀድዎ ፡ ፲ወ፪ ፡ እደው ። ረስጣ ፡ ፲ወ፫ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ መካነ ፡ ምእመናን ፡ ዘውስቴቱ ፡ ኅዳጣን ፡ ወኢበዝኁ ፡ ማኅበር ፡ ከመ ፡ ይግ በሩ ፡ ሢመተ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ እስከ ፡ መጠነ ፡ ፲ወ፪ ፡ እደው ፡ ለይጽሐፉ ፡ ኀበ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘቅርብት ፡ ብሔር ፡ ኀበ ፡ ሀለዉ ፡ ውስቴታ ፡ አምመናን ፡ ብዙኃን ፡ ከመ ፡ ይም ጽኡ ፡ እምእመናኒሆሙ ፡ ፫ቱ ፡ እለ ፡ ተኅርዩ ፡ ወያምክርዎሙ ፡ በአስተሐምሞ ፡ በእንተ ፡ ዘይደልዎ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ሎቱ ፡ ሒረት ፡ ሠናይ ፡ ዘኢፀራፊ ፡ ወዘኢያደሉ ፡ ወዘይክል ፡ ተርጕሞ ፡ መጻሕፍት ።

፺፪ ወግብራትስ ፡ እለ ፡ ይከልእ ፡ ስሱ ፡ እማንቱ ፡ ቀዳሚት ፡ ረስጠጅ ፡ ፶ወ፪ ፡ ኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘጋኔን ።

፺፫ ካልእት ፡ ወሣልሲት ፡ ረስጠጅ ፡ ፶ወ፱ ፡ ወኢይ ደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ዕዉር ፡ ወኢጽሙም ፡ ወኢዝንጉዕ ፡ እኮ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ነውር ። አላ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ኢይክል ፡ በእንተ ፡ ፈጽሞቱ ፡ ለዘውእቱ ፡ ይትፈቀድ ፡ እምግብራተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

፺፬ ራብዕ ፡ ረስጠጅ ፡ ዘ፸ወ፫ ፡ ወዘኢኮነ ፡ ምእ መነ ፡ ወተጠምቀ ፡ ወዘነበረ ፡ ብእሴ ፡ እኩየ ፡ ወነስሐ ፡ ኢይሠየም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በቀዳሚ ፡ ግብሩ ። እስመ ፡ ውእቱ ፡ እምአበሳ ፡ ኢይኩን ፡ መምህረ ፡ ወኢተአምረ ፡ ኂሩቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ለእመ ፡ ይከውን ፡ ውእቱ ፡ በአእምሮ ፡ እምእግ ዚአብሔር ።

፺፭ ኃምስ ፡ ረስጠጅ ፡ ፲ወ፫ ፡ ወዘኀጸወ ፡ ርእሶ ፡ በፈቃዱ ፡ ኢይሠየም ። ወዘተኀጽወ ፡ በትዕ ግልት ፡ ኢይትከላእ ፡ በእንተ ፡ ውእቱ ።

፺፮ ሳድስ ፡ ጠስ ፡ ፳ወ፫ ፡ ወለእመ ፡ ተዓደቀ ፡ ሎቱ፡ ፩ ፡ ወይቤ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ኢይረትዕ ፡ ለኤጲስ ቆጶስና ፡ ለይደኅር ፡ ግብሩ ፡ ፫ተ ፡ አውራኀ ። ወእምዝ ፡ ይትከሠት ፡ በእንቲአሁ ፡ ግብሩ ፡ በሀላዌ ፡ ዕድዉ ፡ አው ፡ በኢሀላዌሁ ። ወለእመ ፡



መዓርጉ ፡ ከመዓርግ ፡ ወደ ፡ ማዕርግ ፡ ያው ጡት ። በአካሄዱ ፡ ሁሉ ፡ በሚገባው ፡ መዓርግ ፡ ጸንቶ ፡ ቢኖር ፡ ያንጊዜ ፡ ይሹሙት ።

፺፩ ስምንተኛ ፡ ከብዙ ፡ ሰዎች ፡ ይመረጥ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። በስ ፡ ፹ወ፯ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ፲ወ፪ ፡ ሰዎች ፡ ሳይ መስክሩለት ፡ አይሾም ። ረስጣ ፡ ፲ወ፫ ፡ የምእመ ናኑ ፡ ቦታ ፡ በውስጡ ፡ ያሉበት ፡ ሰዎች ፡ ጥቂ ቶች ፡ ቢሆኑ ፡ ኤጲስቆጶሱን ፡ ለመምረጥ ፡ ሰዎቹ ፡ እስከ ፡ ፲ወ፪ ፡ ያልመሉ ፡ ቢሆኑ ፡ ብዙዎ ች ፡ ምእመናን ፡ ወዳሉበት ፡ በአቅራቢያቸው ፡ አገር ፡ ወደምትገኝ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከምእ መናኖቻቸው ፡ ወገን ፡ የተመረጡ ፡ ፫ት ፡ ሰዎች ይመጡ ፡ ዘንድ ፡ ይጻፉ ። የሚገባውንም ፡ ለመ ምረጥ ፡ ያማክሯቸው ። መልካም ፡ አኗኗር ፡ ያለው ፡ እንደሆነ ፡ የማይሳደብ ፡ የማያደላ ፡ መጻሕፍትን ፡ መተርጐም ፡ የሚችል ፡ እንደ ሆነ ፡ ያማክሯቸው ።

፺፪ ከሹመት ፡ የሚከለክሉ ፡ ነገሮች ፡ ስድስት ፡ ናቸው ። መጀመሪያዪቱ ፡ ረስጠጅ ፡ ፶ወ፪ ። ጋኔን፡ ያደረበት ፡ ሰው ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ መሆን ፡ አይገ ባውም ።

፺፫ ሁለተኛዪቱና ፡ ሦስተኛዪቱ ፡ ረስጠጅ ፡ ፶ወ፱ ። ዓይነ ፡ ስውር ፡ ደንቆሮ ፡ ዝንጉዕ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሊሆን ፡ አይገባውም ። ነውር ፡ ሆኖ ፡ አይደለም ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥራ ፡ ወገን ፡ ከርሱ ፡ የሚሻውን ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡ ስለማይችል ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፺፬ አራተኛው ፡ ረስጠጅ ፡ ፸ወ፫ ፡ አማኒ ፡ ያይደለ ፡ በኋላ ፡ የተጠመቀ ፡ ክፉ ፡ ሁኖ ፡ ኑሮ ፡ በኋላ ፡ የተመለሰ ፡ ሰው ፡ ከበደል ፡ ወገን ፡ ስለሆነ ፡ በቀደመ ፡ ሥራው ፡ ኤጲስቆጶስነት ፡ አይሾም ። ደግነቱ ፡ ሳይታወቅ ፡ አስተማሪ ፡ አይሁን ። ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ምልክት ፡ ካልተገኘ ለት ፡ በቀር ።

፺፭ አምስተኛው ፡ ረስጠጅ ፡ ፲ወ፫ ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ አባለ ፡ ዘሩን ፡ የሰለበ ፡ አይሾም ። በግድ ፡ የተ ሰለበ ፡ ግን ፡ በግድ ፡ ስለሆነ ፡ አይከልከል ።

፺፮ ስድስተኛው ፡ ጠስ ፡ ፳ወ፫ ፡ አንዱ ፡ አንዱን ፡ ለኤጲስቆጶስነት ፡ አይገባም ፡ ብሎ ፡ ቢከሰው ፡ ሥራው ፡ ፫ወር ፡ ይቈይ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ባላ ጋራው ፡ ባለበት ፡ ወይም ፡ በሌለበት ፡ ሥራው ፡ ስለርሱ ፡ ይመርመር ። በመጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡

ተዐውቀ ፡ ላዕሌሁ ፡ ግብር ፡ ዘይከልእ ፡ በውስተ ፡ ቀኖናት ፡ እምተሠይሞቱ ፡ ይትከላእ ። ወእመ ፡ አኮሰ ፡ ለይሠየም ፡ ወዕድውኒ ፡ ዘእስተዋድዮ ፡ ወኢያቀመ ፡ ላዕሌሁ ፡ ዘዘከሮ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ካህነ ፡ ለይሰደድ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ሕዝባዌ ፡ ለይትገሠፅ ፡ በከመ ፡ ይደሉ ።

፲ ወሣልስ ፡ ዘኢይደሉ ፡ ወኢይከልእ ፡ ረስጠጅ ፡ ፳ወ፪ቱ ፡ ወኢይትከላእ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ነዳር ፡ ወኢሐንካስ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ይሜኒ ፡ ለዝግብር ። እስመ ፡ ነውረ ፡ ሥጋ ፡ ኢኮነ ፡ ነውረ ፡ ወባሕቱ ፡ ነውርሰ ፡ ነውረ ፡ ነፍስ ፡ ውእቱ ።

፲፩ ወገጽ ፡ ካልእ ፡ ግብረ ፡ ሢመቱ ። ድስቅ ፡ ፴ወ፯ቱ ፡ ወይሠየም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ወኵሎሙ ፡ ሰብእ ፡ ይነብሩ ፡ በእንተ ፡ ተሠይሞቱ ፡ ሕዝብኒ ፡ ወካህናት ፡ እንዘ ፡ ሰምዐ ፡ ይከውኑ ፡ሎቱ ። ወኤጲስቆጶሳትኒ ፡ እለ ፡ መጽኡ ፡ ከመ ፡ ያንብሩ ፡ እደዊሆሙ ፡ ዲቤሁ ፡ ይትኀፀቡ ፡ እደዊሆሙ ፡ ወእምዝ ፡ ይሢምዎ ፡ ወሕዝብ ፡ ቀዊሞሙ ፡ በእርምሞ ፡ ወበፍርሃት ፡ ያንሥኡ ፡ እደዊሆሙ ፡ ወያንብሩ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ እደዊሆሙ ፡ ዲቤሁ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ንሕነ ፡ ናነብር ፡ እደዊነ ፡ ዲበ ፡ ዝንቱ ፡ ገብር ፡ ኅሩይ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከመ ፡ ይቁም ፡ ውስተ ፡ ሥርዓት ፡ ሠናይት ፡ ወጽንዕት ፡ ዘአሐቲ ፡ ዘእንበለ ፡ ነውር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡ ዘኢያስተርኢ ። ለገቢረ ፡ ፍትሐ ፡ ርትዕ ፡ ወከሚት ፡ ለቅዳሴ ፡ ወጸጋ ፡ ንጽሕት ፡ ወምሂር ፡ ምእመን ፡ ዘውእቱ ፡ ዘተሠይመ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጉባኤ ፡ እምኅበ ፡ ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ በምሥጢረ ፡ መስቀል ። ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ያንብር ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ቀዳማዊ ፡ እምኔሆሙ ፡ እዴሁ ፡ ዲቤሁ ። ወይበል ፡ ጸሎተ ፡ ሢመት ፡ ወይበሉ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ አሜን ።

፲፪ ሥርዋጽ ፡ ፩ቱ ፡ ጸሎተ ፡ ሢመትሰ ፡ ሀሎ ፡ ውስተ ፡ ክፍል ፡ ዘዘከርነ ፡ ወነዋ ፡ ተሠርዐ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሐቲ ፡ መጽሐፈ ፡ ሢመት ፡ ወይእቲ ፡ ወካልእቲሃ ፡ ውስቴታ ፡ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ የአምኅዎ ፡ ኤጲስቆጶ



ከሹመት ፡ የሚከለክል ፡ ነውር ፡ ቢገኝበት ፡ ይከልከል ። ይህ ፡ ባይሆን ፡ ግን ፡ ይሾም ፡ የከሰሰውም ፡ ባላጋራ ፡ የከሰሰበትን ፡ ባይረታ ፡ ካህን ቢሆን ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይለይ ። ሕዝባዊ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ እንደሚገባ ፡ ይቀጣ ።

፲ ሦስተኛው ፡ ለሹመት ፡ የማያበቃውንና ፡ የማይከለክለውን ፡ ይናገራል ። ረስጠጅ ፡ ፳፪ ፡ እንድ ዓይና ፡ ወይም ፡ እንካሳ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ለዚህ ፡ ሥራ ፡ ተስማሚ ፡ ከሆነ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ከመሆን ፡ አይከልከል ። የአካል ፡ ጕድለት ፡ ነውር ፡ አይደለምና ። ነውርስ ፡ የነፍስ ፡ ነውር ፡ ነው ።

፲፩ ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ የሹመቱን ፡ ሥራ ፡ ይናገራል ። ድስቅ ፡ ፴፯ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ ይሾም ። በሚሾምበትም ፡ ቀን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ይገኙ ። ሕዝብና ፡ ካህናት ፡ መስክረውለት ፡ ይሾም ። እጃቸውን ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ሊያኖሩ ፡ የመጡ ፡ ኤጲስቆጶሳትም ፡ እጃቸውን ፡ ይታጠቡ ። ከዚያ ፡ በኋላም ፡ ይሹሙት ። ሕዝቡም ፡ በፍርሃትና ፡ በጸጥታ ፡ ቁመው ፡ እጃቸውን ፡ ያንሡ ። ኤጲስቆጶሳቱም ፡ "እኛ ፡ በዚህ ፡ በተመረጠ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ ላይ ፡ እጃችንን ፡ እናስቀምጣለን" ፡ እያሉ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ስም ፡ እጃቸውን ፡ ያስቀምጡ ። ነውር ፡ በሌለባትና ፡ እንዲት ፡ በሆነች ፡ በማይገለጥ ፡ በሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በጸናች ፡ ሥርዓት ፡ ይጸና ፡ ዘንድ ። የቀና ፡ ፍርድን ፡ ለመፍረድ ፡ ምስጋናን ፡ ለማቅረብ ፡ ልጅነትን ፡ ለማስጠት ፡ ለታመኑች ፡ ትምህርት ፡ ይኸውም ፡ ነገረ ፡ መስቀልን ፡ ለማስተማር ፡ ከሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘንድ ፡ በጉባኤ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተሾመ ፡ ነው ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከነርሱ ፡ ቀዳሚ ፡ የሆነው ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እጁን ፡ ይጫንበት ። የሹመቱንም ፡ ጸሎት ፡ ያድርስ ። ሕዝቡም ፡ አሜን ፡ ይበሉ ።

፲፪ ሥርዋጽ ፡ ፩ ። የሹመት ፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ አስቀድመን ፡ በተናገርነው ፡ ክፍል ፡ አለ ። በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ እንዲት ፡ የሹመት ፡ መጽሐፍ ፡ እነሆ ፡ ተጽፋለች ። እርሷና ፡ ሌሎችም ፡ በውስጧ ፡ ይገኛሉ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ኤጲስቆ

ሳት ፡ ወይበሉ ፡ ኵሎሙ ፡ ካህናት ፡ ወሕዝብ ፡ ይደልዎ ፡ ይደልዎ ፡ ይደልዎ ። ወየአምኅዎ ፡ ኵሎሙ ፡ ወያስተብቍዑ ፡ ሎቱ ፡ ሰላመ ። ወእምዝ ፡ ያንብቡ ፡ ክፍላተ ፡ ዘይደሉ ፡ ወይፈጽሙ ፡ ቅዳሴ ፡ በእስተታልዎ ፡ ወይትመጠው ፡ ውእቱ ፡ ቅድመ ፡ እምሥጢራተ ፡ ቅድሳት ።

ወእምዝ ፡ የሀበሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ እምኔሃ ፡ በበ መዓርጊሆሙ ፡ ወይፈንዎሙ ፡ በሰላም ፡ ወያ ብስሉ ፡ ፫ተ ፡ መዋስለ ፡ በዓለ ፡ መንፈሳዊተ ፡ በአምሳለ ፡ ምሥጢሩ ፡ ለዘተንሥአ ፡ በሣል ስት ፡ ሰለት ።

፻፫ ረስጠብ ፡ ፶ወ፪ቱ ፡ ወእምእመ ፡ ሠምርዎ ፡ ኵሎሙ ፡ ይትጋብኡ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ወቀሳ ውስት ፡ ወኤጲስቆጶሳት ፡ በሰለተ ፡ እሑድ ፡ ወይሰእሎሙ ፡ ዘየዐቢ ፡ እምኔሆሙ ፡ ለቀሳው ስት ፡ ወዲያቆናት ፡ ወይበል ፡ ዝንቱኑ ፡ ዘሠመ ርክምዎ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ሊቀ ፡ ለክሙ ። ወሶበ ፡ ይቤሉ ፡ እወ ፡ ይሰእሎሙ ፡ ካዕበ ፡ ወይበል ፡ ለዝንቱ ፡ ትደልዎኑ ፡ ሢመት ፡ ክብርት ፡ ወአርትዐኑ ፡ ሐረቶ ፡ በሠናይ ፡ ወበጥዩቅ ፡ ወኢተረክበ ፡ ላዕሌሁ ፡ ምንትኒ ፡ ወሰእመ ፡ ተሠጥውዎ ፡ ኵሎሙ ፡ ወይቤሉ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ከመዝ ፡ እማን ፡ ይደልዎ ፡ ሢመት ፡ በጽድቅ ፡ ወእኮ ፡ በአድልዎ ። ወይሰእሎሙ ፡ ካዕበ ፡ ሣልሰ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ድልውኑ ፡ ውእቱ ፡ በአማን ፡ ለዝንቱ ፡ ሢመት ፡ እስመ ፡ ይቀውም ፡ ኵሉ ፡ ቃል ፡ እምአፈ ፡ ፪ቱ ፡ አው ፡ ፫ቱ ። ወለ እመ ፡ ይቤሉ ፡ በሣልስ ፡ ድልው ፡ ውእቱ ፡ ይሰ ፍሑ ፡ ወያስተማፍሑ ፡ እደዊሆሙ ፡ ኵሎሙ ። ወሶበ ፡ ገብሩ ፡ ዘንተ ፡ በተሰናእዎ ፡ ለይኩን ፡ እርምሞ ፡ ወዲያቆናትኒ ፡ ይፁሩ ፡ ወንጌላተ ፡ ቅዱሳተ ፡ ወውእቶን ፡ እንዘ ፡ ክሡታት ፡ ዲበ ፡ ርእሱ ፡ ለዘይሠይምዎ ፡ ወያንብርዎ ፡ ኤጲስ ቆጶሳት ፡ ዲበ ፡ መንበር ፡ ዘድልው ፡ ሎቱ ፡ ወእምከመ ፡ ተወክፍዎ ፡ ኵሎሙ ፡ እግዚአብ ሔርኒ ፡ ተወክፎ ።

፻፬ በስ ፡ ፵ወ፮ቱ ፡ ወኢይሠየም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘእ ንበለ ፡ ይምጻእ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እምሀገር ፡ ወእኮ ፡ ውእቱ ፡ ባሕቲቱ ፡ አላ ፡ ፪ቱኒ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ካልአን ፡ ምስሌሁ ። ወይሠየም ፡ እምነበ ፡ ፫ቱ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ወከመዝ ፡ ይሠየም ፡ እንዘ ፡ ይፀ ውሩ ፡ ወንጌለ ፡ ዲበ ፡ ርእሱ ። ወይጸሊ ፡ ላዕ ሌሁ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘየዐቢ ፡ ከመዝ ። ወሶበ ፡



ጳሳቱ ፡ እጅ ፡ ይንሡት ። ሕዝቡና ፡ ካህናቱም ፡ ይገባዋል ፡ ይገባዋል ፡ ይገባዋል ፡ ይበሉ ። ሁላ ቸውም ፡ እጅ ፡ ይንሡት ። በእንተ ፡ ሰላምን ፡ ይጸ ልዩለት ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሊነበብ ፡ የሚገባውን ፡ ክፍል ፡ ያንብቡ ። እከታትለውም ፡ ቅዳሴውን፡ ይፈጽሙ ። አስቀድሞ ፡ እርሱ ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ይቀበል ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በየማዕርጋ ቸው ፡ ለሁሉም ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ያቀብላ ቸው ። በሰላምም ፡ ያሰናብታቸው ። በሦስተኛ ፡ ቀን ፡ በተነሣው ፡ በጌታ ፡ ትንሣኤ ፡ አምሳል ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ መንፈሳዊ ፡ በዓልን ፡ ያከብሩ ።

፻፫ ረስጠብ ፡ ፶፪ ። ሁሉም ፡ ከመረጡት ፡ በኋላ ፡ ሕዝቡና ፡ ቀሳውስቱ ፡ ዲያቆናቱ ፡ ኤጲስቆጶሳ ቱም ፡ በሰለተ ፡ እሑድ ፡ ይሰብሰቡ ። ከነርሱ ፡ የሚበልጠው ፡ አለቃ ፡ ይህናችሁ ፡ ዘንድ ፡ የመ ረጣችሁት ፡ ይህ ፡ ነውን ፡ ብሎ ፡ ቀሳውስቱ ንና ፡ ዲያቆናቱን ፡ ይጠይቃቸው ። አዎን ፡ ቢሉ የከበረችው ፡ ሹመት ፡ ለዚህ ፡ ትገባዋለችን ፡ ይበል ። በሚገባና ፡ በተረዳ ፡ ሥርዓት ፡ አኗኗ ሩን ፡ አጽንቷልን ፡ ምንም ፡ በደል ፡ አልተገኘ በትምን ፡ ይበል ። እነርሱም ፡ መልሰው ፡ እን ደዚህ ፡ እንደሆነ ፡ ቢናገሩ ፡ በማድላት ፡ ያይደለ በእውነት ፡ ሹመት ፡ ይገባዋል ። ሦስተኛ ፡ ደግ ሞ ፡ ለዚህ ፡ ሹመት ፡ በእውነት ፡ ይገባ ልን ፡ ብሎ ፡ ይጠይቃቸው ። ነገር ፡ ሁሉ ፡ በሁ ለት ፡ ወይም ፡ በሦስት ፡ ምስክር ፡ ይጸናልና ። በሦስተኛውም ፡ ጊዜ ፡ ይገባዋል ፡ ቢሉ ፡ ሁሉ ም ፡ እጃቸውን ፡ ዘርግተው ፡ ያጨብጭቡ ። ይህ ንን ፡ በስምምነት ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ ጸጥታ ፡ ይሁን ። ዲያቆናትም ፡ ቅዱሳት ፡ ወንጌላትን ፡ ገልጠው ፡ በተሾመው ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ይያዙ ። ኤጲስቆጶሳቱም ፡ ለርሱ ፡ በሚገባው ፡ ወምበር ፡ ያስቀምጡት ። ሁሉም ፡ ከተቀበሉት ፡ እግዚአ ብሔርም ፡ ይቀበለዋል ።

፻፬ በስ ፡ ፵፮ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ከሌላ ፡ አገር ፡ ሳይ መጣ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አይሾም ። እርሱ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። ሌሎችም ፡ ሁለት ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይኑሩ ። በሦስት ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ይሾም ። እንደዚህ ፡ ይሾም ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ወን ጌልን ፡ ተሸክመው ፡ የበለጠው ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እንደዚህ ፡ ይጸልይ ። ጸሎቱን ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ፡

ፈጸመ ፡ ያንብር ፡ እዴሁ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወይስዓሞ ፡ ወይንፋሕ ፡ ውስተ ፡ ገጹ ፡ ከመ ፡ ይትመላእ ፡ ላዕሌሁ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ። ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ የእምኅዎ ፡ እለ ፡ ተርፉ ፡ ካህናት ፡ ወጸታ ፡ ሕዝብስ ፡ ይስዓሙ ፡ እዴሁ ፡ ወኢየእምኑ ፡ እፉሁ ፡ ዘእንበለ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ወቀሳውስት ፡ እምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ይፈጽሙ ፡ ቀዳሴ።

፻፭ ድስቅ ፡ ፴ወ፩ቱ ፡ ወንኤዝዘክሙ ፡ ከመ ፡ ይሠየም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እም፫ቱ ፡ ኤጲስቆጶሳት ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዓጸባ ፡ እም፪ቱ ፡ ኤጲስቆጶሳት ። ወኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይሠየም ፡ ለከሙ ፡ እም፩ዱ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እስመ ፡ ስምዐ ፡ ፪ቱ ፡ አው ፡ ፫ቱ ፡ ይከውን ፡ ቀዋሚ ። ረስጣ ፡ ፵ወ፰ቱ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ውእቱ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አሐዱ ፡ ዘአንበረ ፡ እደዊሁ ፡ ላዕሌሁ ፡ ይትፈለጥ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዝንቱ ፡ በእንተ ፡ ዓጸባ ፡ በግብር ፡ ወለእመ ፡ ኢተክህለ ፡ ከመ ፡ ይትጋብኡ ፡ ማኅበር ፡ በእንተ ፡ ስደት ፡ ዘለወቀ ፡ አው ፡ በምክንያት ፡ ካልእ ፡ ዘከመዝ ፡ ወይኩን ፡ ዘተንእደ ፡ እምብዙኃን ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ወያብሕዎ ፡ ሎቱ ፡ ዘንተ ፡ ወይኩን ፡ በትእዛዞሙ ።

፻፮ ወገጸ ፡ ግልስ ፡ እምድኅረ ፡ ተሠይሞቱ ፡ ወዝንቱ ፡ ይትከፈል ፡ ኀበ ፡ ፫ቱ ፡ መክፈልታት ፡ ቀዳሚ ፡ ዘይደልዎ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ በርእሱ ። ድስቅ ፡ ፳ወ፫ቱ ፡ ወእምከመ ፡ ተሠይመ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ይንበር ፡ ፫ተ ፡ ሰባዔያተ ፡ በጾም ፡ ወኢይጥዐም ፡ ምንተኒ ፡ ዘእንበለ ፡ በዕለተ ፡ ሰንበት ፡ እምኑ ፡ ኵሉ ፡ ሰባዔ ፡ ዝንቱ፡ ለእመ ፡ ኢኮነ ፡ በመዋዕለ ፡ ፶ ፡ እምዝኒ ፡ ይፈጽም ፡ ይእተ ፡ ዓመተ ፡ በጾም ፡ በበ ፡ ሠለስቱ ፡ ሠለስቱ ።

፻፯ ሥርዋጽ ፡ ፭ቱ ፡ ይመስለኒ ፡ ዘይቤ ፡ ከመ ፡ ይጹም ፡ ሰለኵሉ ፡ ዕለት ፡ እስከ ፡ ተፍጻሜተ ፡ መዓልት ፡ እምዕለተ ፡ ሰንበት ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ሰንበት ፡ ፫ተ ፡ ሰባዔ ። ወዘተርፈ ፡ ዓመተ ፡ ይጹም ፡ በበኵሉ ፡ ሰባዔ ፡ ፫ተ ፡ ዕለታተ ፡ ረቡዐ ፡ ወዓርበ ፡ ወሰኑየ ። እስመ ፡ በሰንበት ፡ ወበእሑድ ፡ እልቦ ፡ ጾም ፡ ወኢይትፌጸምኒ ፡ ዘበኵሉ ፡ ሰባዔ ፡ በጸዊም ፡ በበ፫ቱ ፡ ፫ቱ ፡ ዕሙረ ፡ እላ ፡ ዘይትፌጸምስ ፡ በትርጓሜ ፡ ዘቀደመ ፡ ዘከሮቱ ።

፻፰ ወይኩን ፡ መብልዑ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ዘይበልዕ ፡



እጁን ፡ ይጫንበት ፡ ይሳመውም ። መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ይመላበት ፡ ዘንድ ፡ በፊቱ ፡ እፍ ፡ ይበልበት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የቀሩት ፡ ካህናት ፡ እጅ ፡ ይንሡት ። ሕዝቡ ፡ ግን ፡ እጁን ፡ ይሳሙት ። ከኤጲስቆጶሳቱና ፡ ከቀሳውስቱ ፡ በቀር ፡ አፉን ፡ አይሳሙት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቅዳሴውን ፡ ይፈጽሙ ።

፻፭ ድስቅ ፡ ፴፩ ። ኤጲስቆጶስ ፡ ከሦስት ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ይሾም ፡ ዘንድ ፡ እናዝዛችኋለን ። የችግር ፡ ዘመን ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ከ፪ኤጲስቆጶሳት ፡ ይሾም። ከአንድ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ግን ፡ ሊሾምላችሁ ፡ አይገባም ። የሁለትና ፡ የሦስት ፡ ምስክርነት ፡ የጸና፡ ይሆናልና ። ረስጣ ፡ ፵፰ ። አንድ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ብቻውን ፡ የሾመ ፡ ከሆነ ፡ ይለይ ። ይህ ፡ በችግር ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፡ በታወቀ ፡ ስደት ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ በሌላ ፡ ምክንያት ፡ ማኅበር ፡ ለመሰብሰብ ፡ ባይችሉ ፡ በብዙዎች ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ የተመሰገነ ፡ ይሁን። ይህንንም ፡ በትእዛዛቸው ፡ ይፍቀዱለት ።

፻፮ ሦስተኛውም ፡ ክፍል ። ከተሾመ ፡ በኋላ ፡ የሚሠራውን ፡ ይናገራል ። ይኸውም ፡ በ፬ ፡ ክፍሎች ፡ ይከፈላል ። መ፩መሪያው ፡ ለራሱ ፡ ሊሠራው ፡ የሚገባውን ፡ ይናገራል ። ድስቅ ፡ ፳፫ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ከተሾመ ፡ በኋላ ፡ ሦስት ፡ ሱባዔ ፡ ይጹም ። በሰለተ ፡ ሰንበት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሱባዔውን ፡ ሁሉ ፡ ምንም ፡ ሳይቀምስ ፡ ይጹም። ይህም ፡ የሚሆነው ፡ ሹመቱ ፡ በበዓለ ፡ ፶ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ነው ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ይህችን ፡ ዓመት ፡ በሳምንቱ ፡ ውስጥ ፡ ፫ ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ እየጾመ ፡ ይጨርስ ።

፻፯ ሥርዋጽ ፡ ፭ ። ከዕለተ ፡ ሰንበት ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ሰንበት ፡ ድረስ ፡ ሦስቱን ፡ ሱባዔ ፡ እስከ ፡ ፲፪ ፡ ሰዓት ፡ ይጹም ፡ ያለ ፡ ይመስለኛል ። በዕለተ ፡ ቀዳሚትና ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ ጾም ፡ የለምና ። የቀረውን ፡ ዓመት ፡ ግን ፡ በሳምንት ፡ ፫ቱን ፡ ቀን ፡ ረቡዕን ፡ ዓርብንና ፡ ሰኞን ፡ ይጹም ፡ ያለ ፡ ይመስለኛል ። በየሱባዔው ፡ ሦስት ፡ ሦስቱን ፡ እንድ ፡ ወገን ፡ አድርጎ ፡ በመጾም ፡ አይፈጸምም ። የሚፈጸምስ ፡ አስቀድመን ፡ በተናገር ነው ፡ ትርጓሜ ፡ ቢሆን ፡ ነው ።

፻፰ ኤጲስቆጶስ ፡ በጾሙ ፡ ወራት ፡ የሚመገበው ፡

በዓመተ ፡ ጾሙ ፡ ኅብስት ፡ ወጼው ፡ ወዘይት ፡
ወመዓር ፡ ወአሕማላተ ፡ ምድር ፡ ወይነሰ ፡ ኢይ
ጥዐም ፡ ወበተረፈ ፡ መዋዕለ ፡ ሕይወቱሰ ፡
ይጹም ፡ በአምጣነ ፡ ክሂሎቱ ። ወይትመጦ ፡
እምነ ፡ መብልዕ ፡ ዘዓጸባ ፡ መጠነ ፡ ዓቅሙ ፡
ወኢይብላዕ ፡ ሥጋ ፡ ለዓለም ፡ እኮ ፡ እስመ ፡
ውእቱ ፡ ለእመ ፡ በልዖ ፡ ዘያረኵሶ ፡ አላ ፡ ከመ ፡
ኢይግዝፍ ፡ ልቡ ፡ ወኢይጽልም ፡ አእምሮቱ ፡
ወኢይትከሀሎ ፡ ከመ ፡ ይትጋሀ ፡ በዕረፍት ።
እስመ ፡ ዘየኀሥሥ ፡ ከመ ፡ ይፈጽም ፡ ዘንተ ፡
ግብረተ ፡ ከመዝ ፡ ይኅረይ ፡ ሎቱ ፡ ጽሙና ፡
ወዘይትዌከፍ ፡ ጽሙና ፡ ኢይትዌከፍ ፡ ሎቱ ፡
ረባኅ ፡ ከመ ፡ ይትመጦ ፡ ዘያጸንዕ ፡ ሥጋ ።
፻፱ ወለእመ ፡ ደወየ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በይእቲ ፡
ዓመት ፡ ደዌ ፡ ዘኢይትከሀሎ ፡ በእንቲአሁ ፡
ከመ ፡ ይፈጽም ፡ ዘብህልናሁ ፡ ይብላዕ ፡ ዓሣ ፡
ወይስተይ ፡ እምወይን ፡ በዓቅም ፡ ኅዳጠ ፡ መዋ
ዕለ ፡ ከመ ፡ ኢይኩን ፡ ውዱቀ ፡ ወኢትኅጣእ ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ምግብናሁ ፡ ወትምህርቶ ፡
ወይጽሐቅ ፡ ከመ ፡ ይትመጦ ፡ በኵሉ ፡ ዕለት ፡
ምሥጢራተ ፡ ለእመ ፡ ኢክልአ ፡ ምክንያት ፡
ከመ ፡ ይሕየው ፡ ባቲ ፡ በኵሉ ፡ ዘመን ።
፻፲ ረስዓ ፡ ፴ወ፺ቱ ፡ ወኢይደልዎ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡
ከመ ፡ ይጹም ፡ ዘእንበለ ፡ በዕለት ፡ ዘይጸውሙ ፡
ቦቱ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ። እስመ ፡ ውእቱ ፡ ለእመ ፡
መጽአ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወአምጽአ ፡
አሐዱ ፡ ምንተኒ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይት
ፈቀድ ፡ ከመ ፡ ይብላዕ ፡ ምስለ ፡ ማኅበር ።
፻፲፩ ድስቅ ፡ ፱ቱ ፡ ወይትመጦ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እመ
ብልዕ ፡ ወመስቴ ፡ ዘየአክሎ ፡ ለሕይወቱ ፡ ከመ፡
ይክሀል ፡ ወከመ ፡ ኢይትሀከይ ፡ ምሂሮቶሙ ፡
ለእለ ፡ ኢኮኑ ፡ ምሁራነ ፡ ወኢያስተዋፅእ ፡
ብዙኀ ፡ ወኢይኩን ፡ ፍሉሰ ፡ ወኢዘያንጌጊ ፡
ወሑረቱኒ ፡ ኢይኩን ፡ በትፍግዕት ። ወኢይብ
ላዕ ፡ ምንተኒ ፡ ኅሩየ ፡ ወይኩን ፡ ሕያወ ፡ ልብ ፡
በውስተ ፡ ትምህርት ፡ ወይምሀር ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ፡
ወያንብብ ፡ መጻሕፍተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይ
ጠይቅ ፡ አከፋለ ፡ ከመ ፡ ይተርጕም ፡ መጻሕ
ፍተ ፡ በጥያቄ ፡ ወይተርጕም ፡ ወንጌለ ፡ ወይተ
ርጕም ፡ አሪተ ፡ ወነቢያተ ። ይቤ ፡ እግዚእ ፡
"ኅሡ ፡ ትርአዩ ፡ መጻሕፍተ ፡ እስመ ፡ እማንቱ፡
ስምዐ ፡ ይከውና ፡ በእንቲአየ" ። ወኢይፍቅድ ፡
ረባኀ ፡ ማኅበር ፡ ዘያስተኃፍር ፡ ፈድፋደሰ ፡

ምግብ ፡ ዳቦ ፡ ጨው ፡ ዘይት ፡ ማር ፡ ቅጠላቅ
ጠል ፡ ይሁን ። ወይን ፡ ግን ፡ አይጠጣ ። በቀረ ፡
ዘመኑ ፡ ግን ፡ በተቻለው ፡ መጠን ፡ ይጹም ።
ከምግብ ፡ ለዐቅመ ፡ ሥጋ ፡ ያህል ፡ ይመገብ ፡
ሥጋ ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡ አይብላ ። ቢበላው ፡
የሚያረክሰው ፡ ሁኖ ፡ አይደለም ። ልቡናው ፡
እንዳይደነድን ፡ አእምሮው ፡ እንዳይዝግ ፡ በዕ
ረፍት ፡ ሁኖ ፡ ለሥራ ፡ ለመትጋት ፡ ስለማይቻ
ለው ፡ ነው ፡ እንጂ ። ይህን ፡ ሥራ ፡ ለመፈጸም ፡
የሚሻ ፡ ሰው ፡ ከምግብ ፡ መለየት ፡ ያሻዋልና ።
ጽሙናንም ፡ የተቀበለ ፡ ሰው ፡ ትርፍ ፡ ገንዘብ ፡
አይሻምና ፡ ለቁመተ ፡ ሥጋ ፡ ያህል ፡ መቀበል ፡
ይገባዋል ፡ እንጂ ።
፻፱ ኤጲስቆጶስ ፡ ያዘዝነውን ፡ ይፈጽም ፡ ዘንድ ፡
የማያስችለው ፡ ደዌ ፡ በዚችው ፡ ዓመት ፡ ቢታ
መም ፡ ዓሣ ፡ ይብላ ። ወይንም ፡ በመጠኑ ፡
ይጠጣ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ወድቆ ፡ እንዳይኖር ።
ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ አስተዳደሩንና ፡ ትምህር
ቱን ፡ እንዳታጣ ። ምክንያት ፡ ካልከለከለው ፡
በቀር ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡
ለመቀበል ፡ ይትጋ ። ባለው ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡
ሕያው ፡ ሁኖ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ።
፻፲ ረስጣ ፡ ፴፺ ። ሕዝቡ ፡ በሚጾምበት ፡ ጊዜ ፡
ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ መጾም ፡ አይገባ
ውም ። እርሱ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቢመጣ፡
አንድ ፡ ሰውም ፡ ምግብ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ
ያን ፡ ቢያመጣ ፡ ከማኅበሩ ፡ ጋር ፡ ይበላ ፡ ዘንድ፡
ይገባዋልና ።
፻፲፩ ድስቅ ፡ ፱ ። ኤጲስቆጶስ ፡ ከምግብና ፡ ከመጠጥ ፡
ለቁመተ ፡ ሥጋ ፡ ያህል ፡ ይውሰድ ። ያልተማሩ
ትን ፡ ለማስተማር ፡ እንዲችል፡ ቸልም ፡ እንዳ
ይል ፡ አብዝቶም ፡ አያወጣጣ ፡ ዘዋሪ ፡ ሰውንም
የሚበድል ፡ አይሁን ። አኗኗሩም ፡ በተድላ ፡
በደስታ ፡ አይሁን ። የላመ ፡ የጣመ ፡ አይቅመስ ።
በማስተማር ፡ ጊዜ ፡ ትጉ ፡ ይሁን ፡ ዘወትር ፡
ያስተምር ። የእግዚአብሔርንም ፡ መጻሕፍት ፡
ይመልከት ። መጻሕፍትን ፡ አስረድቶ ፡ ይተረ
ጕም ፡ ዘንድ ፡ ክፍል ፡ ክፍሉን ፡ በጥያቄ ፡ ለይቶ
ይወቀው ። ወንጌልን ፡ ኦሪትንና ፡ ነቢያትን ፡
ይተርጕም ። ጌታችን ፡ "መጻሕፍትን ፡ ተመል
ከቱ ፡ እነርሱ ፡ ስለኔ ፡ ይመሰክራሉና" ፡ አለ ።
(ዮሐ ፡ ፭ ፡ ፴፱ )። የሚያሳፍር ፡ የማኅበርን ፡
ትርፍ ፡ አይውደድ ። ይልቁንም ፡ ከዓላውያን ፡

ምስለ ፡ ዓላውያን ። ወኢይፍቅድ ፡ መክፈልተ ፡ ዘየዐቢ ፡ ወኢይኩን ፡ ተዓጋሤ ፡ ወኢመፍቀሬ ፡ አብዕልት ፡ ወጸላኤ ፡ ነዳያን ፡ ወኢያፍቅሮ ፡ በዓለ ፡ ውዴት ፡ ወኢይኩን ፡ ስምዐ ፡ በሐሰት ፡ ወኢቀኖጡዐ ፡ ወኢይትሐበይ ፡ ፅደኒ ፡ ወኢያፍቅር ፡ ሢመተ ፡ ወኢይኩን ፡ ዘ፪ኤ ፡ ልቡ ፡ ወ፪ኤ ፡ ልሳኑ ፡ ወኢስማዔ ፡ ወኢይሑር ፡ ኀበ ፡ በዓላተ ፡ አሕዛብ ፡ ወኢፈታዊ ፡ ወኢመፍቀሬ ፡ ንዋይ ። እስመ ፡ እሉ ፡ ግብራት ፡ ኵሎሙ ፡ ጸላእቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወስቱፋኒሆሙ ፡ ለሰይጣናት ። ወይኩን ፡ ጠቢበ ፡ ወለባዌ ፡ ከመ ፡ ያእምር ፡ እኩየ ፡ ወይትዐቀብ ፡ እምኔሁ ፡ ወይኩን ፡ ፍቁረ ፡ ለኵሉ ፡ ወለኵሉ ፡ ግብር ፡ ሠናይ ፡ ዘሀሎ ፡ ላዕለ ፡ ሰብእ ፡ ለይርብኖ ፡ ለነፍሱ ፡ እስመ ፡ ኖላዊ ፡ ለእመ ፡ ርኁቀ ፡ እምዓመፃ ፡ ይስሕቦሙ ፡ ለአርዳኢሁ ፡ ወያስተናሥእሙ ፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ ተመሳልያነ ፡ በምግባራቲሁ ፡ ሠናያት ፡ በአማን ። በከመ ፡ ይቤ ፡ ሆሴዕ ፡ ነቢይ ፡ "እስመ ፡ በከመ ፡ ይከውን ፡ ካህን ፡ ከማሁ ፡ ካዕበ ፡ ሕዝብኒ" ፡ ወዓዲ ፡ መምህርነ ፡ ኄር ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክነ ፡ ወጠነ ፡ ቅድመ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ወይምሀር ፡ ወይቤ ፡ "እስመ ፡ ዘይገብር ፡ ወይሜህር ፡ ዐቢየ ፡ ይሰመይ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት" ።

፻፲፪ ዘ፴ወ፰ቱ ፡ ወእምድኅረ ተሠይሞቱ ፡ ይዐመድ ፡ ውስተ ፡ ምሥዋዕ ፡ ወይጸሊ ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ። ወለእመ ፡ ጸለየ ፡ በእንተ ፡ ነፍሱ ፡ ወበእንተ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ በኵሉ ፡ ሰዓት ፡ ሠናየ ፡ ገብረ ። ወየሀሉ ፡ ባሕቲቱ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ሎቱ ፡ ዘየሠምሮ ፡ ለነቢር ፡ ምስሌሁ ፡ እመ ፡ አኮ ፡ አሐዱ ፡ አው ፡ ፪ቱ ፡ ወውእቶሙ ፡ አሐቲ ፡ ነፍስ ፡ ምስሌሁ ፡ ይግበር ፡ በዘይትራድእዎ ፡ በእንተ ፡ ዘይደሉ ። ወፈድፋደስ ፡ ዘየዐቢ ፡ በእንተ ፡ ፍጻሜ ፡ ጸሎት ፡ ወተሰናእዎ ፡ ወበአኀጽሮ ፡ በእንተ ፡ አስተበቍዖተ ፡ ስንእ ፡ አሐዱ ። እስመ ፡ እግዚእነ ፡ ይቤ ፡ "ኀበ ፡ ሀለዉ ፡ ፪ቱ ፡ አው ፡ ፫ቱ ፡ ጉቡእን ፡ በስምየ ፡ እነ ፡ እሄሉ ፡ ምስሌሆሙ" ። ወለእመ ፡ ኢይትከሀሎ ፡ እዝልፎት ፡ ይጸሊ ፡ ሰዓታተ ። ዘ፴ወ፰ቱ ፡ ወያስተብቍዖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በኵሉ ፡ ልብ ፡ ወበኵሉ ፡ ድካም ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ቃሉ ፡ ዘይ



ጋር ፡ የሆነውን ፡ አይውደድ ። አብልጡልኝ ፡ አይበል ። ቀማኛ ፡ አይሁን ፡ ድሆችን ፡ የሚጠላ ፡ ባለጠጎችን ፡ የሚወድ ፡ አይሁን ። ነገረ ፡ ሠሪ ፡ አይውደድ ። በሐሰት ፡ አይመስክር ፡ ቍጡ ፡ አይሁን ፡ ለአንዱ ፡ ሰው ፡ እንኳ ፡ አይዋሽ ፡ ሹመትን ፡ አይውደድ ። ሁለት ፡ ልብ ፡ አይሁን ። ሁለት ፡ ምላስ ፡ አይሁን ። ነገረ ፡ ሠሪን ፡ የሚሰማ ፡ አይሁን ። ወደ ፡ አሕዛብ ፡ በዓል ፡ አይሂድ ። ገንዘብ ፡ ወዳጅ ፡ አይሁን ። ቀማኛም ፡ አይሁን ። እነዚህ ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጠላቶች ፡ የሰይጣናት ፡ ተባባሪዎች ፡ ናቸውና ። ክፉን ፡ አውቆ ፡ ከርሱ ፡ ይጠበቅ ፡ ዘንድ ፡ ብልህና ፡ አስተዋይ ፡ ይሁን ። ለሁሉ ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ የሚወድ ፡ ይሁን ። እርሱን ፡ ራሱን ፡ ይጥቀም ። ጠባቂ ፡ ከዓመፃ ፡ ቢርቅ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ ይስባቸዋልና ። በእውነትም ፡ የበጎ ፡ ምግባር ፡ ተከታዮች ፡ እንዲሆኑ ፡ ያነቃቃቸዋልና ። ነቢዩ ፡ ሆሴዕ ፡ "ካህኑ ፡ እንደ ሆነ ፡ ሕዝቡም ፡ ይሆናል ፡ ብሏልና ። (ሆሴ ፡ ፬ ፡ ፱) ። ዳግመኛም ፡ ደጉ ፡ መምህራችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አስቀድሞ ፡ ሠርቶ ፡ ያስተምር ፡ ጀመረ ።" እየሠራ ፡ የሚያስተምርም ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ታላቅ ፡ ይባላል" ፡ አለ ። (ማቴ ፡ ፭ ፡ ፲፱) ።

፻፲፪ ድስቅ ፡ ፴፰ ። ከተሾመ ፡ በኋላም ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ ፅሙድ ፡ ይሁን ። በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ ይጸልይ ። ስለ ፡ ራሱና ፡ ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ በየሰዓቱ ፡ ቢጸልይ ፡ መልካም ፡ አደረገ ። በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ብቻውን ፡ ይኑር ። ብቻውን ፡ መኖር ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘው ፡ ከሆነ ፡ ይህ ፡ ግን ፡ ባይሆን ፡ ከአንድ ፡ ወይም ፡ ከሁለት ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ይኑር ። እነርሱ ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ናቸውና ። ስለሚገባው ፡ በሚረዱት ፡ ገንዘብ ፡ ያድርግ ። ይልቁንም ፡ የሚበልጠው ፡ በጸሎትና ፡ በስምምነት ፡ በማሳጠርም ፡ አንድ ፡ እግዚእብሔርን ፡ በመለመን ፡ ነው ። ጌታ ፡ "ሁለት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ ሁነው ፡ በኔ ፡ ስም ፡ ተሰብስበው ፡ ካሉበት ፡ እኔ ፡ በመካከላቸው ፡ እኖራለሁ" ፡ (ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፳) ። ብሏልና ። ሳያቋርጥ ፡ መጸለይ ፡ ባይቻለው ፡ በተወሰኑት ፡ ሰዓቶች ፡ ይጸልይ ። ድስቅ ፡ ፴፰ ። በፍጹም ፡ ልብ ፡ በፍጹም ፡ ድካም ፡ እግዚአብሔ

ብሎ ፡ ኪያሁ ፡ ይፍረይ ፡ ውስተ ፡ ስማዕያኒሁ ፡ ፍሬ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ። ዘኗወ፫ቱ ፡ ወኵሎ ፡ ቃለ ፡ ዘይሜህር ፡ ይደልዎ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ያእምር ፡ ወይገብር ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ገብሮ ፡ ቀዳሚ እምቅድመ ፡ ይምሀሮ ፡ ከመ ፡ ያእምር ፡ ዘይብሎ ፡ በኵሉ ፡ ሐተታ ። እስመ ፡ ውእቱ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ የአምር ፡ ዘይብሎ ፡ እለኒ ፡ ይሰምዕዎ ፡ የአምሩ ፡ ዘይብሎሙ ።

ወዳግማዊ ፡ በእንተ ፡ ዘይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይግበር ምስለ ፡ ሕዝቡ ፡ ወዘይኤዝዞሙ ፡ ቦቱ ። ይቤሎ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ለጢሞቴዎስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ረድኡ ፡ ዘ፫ቱ ፡ እስእለከ ፡ አነ ፡ ቀዳሚ ፡ ኵሉ ፡ በምንትኒ ፡ ግብር ፡ ከመ ፡ ታቅድም ፡ አቅርቦ ፡ ስኢል ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጸሎት ፡ ወአስተብቍዖት ፡ ወአኰቴት ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ከመ ፡ ይንበሩ ፡ በትዕግሥት ፡ ወበህድአት ፡ በአርምሞ ፡ ወበፍርሃተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወበንጽሕ ። እስመ ፡ እሎን ፡ ግብራት ፡ ያበጽሓ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማሕየዊ ፡ ዘያፈቅር ፡ ከመ ፡ ይሕየዉ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ወይብጽሑ ፡ ኀበ ፡ አእምሮተ ፡ ጽድቅ ።

ዘ፰ቱ ፡ ወኩኖሙ ፡ አምሳለ ፡ ለምእመናን ፡ ቢቃል ፡ ወገድል ፡ ወበፍቅር ፡ ወበሃይማኖት ፡ ወንጽሕ ፡ እስከ ፡ አመጽእ ፡ ተዐቀብ ፡ በአንብቦ ፡ ወበምሂር ፡ ወበገሥፆ ፡ ወኢታስትት ፡ ጸጋሁ ፡ ዘላዕሌከ ፡ ዘወሀበከ ፡ ምስለ ፡ ተነብዮ ፡ ወምስለ ፡ ሢመተ ፡ እደ፡ሆሙ ፡ ለጳጳሳት ፡ ዑቅ ፡ ወሀሉ ፡ ላዕሌሆሙ ። እስመ ፡ ለእመ ፡ ገበርከ ፡ አንተ ፡ ዘንተ ፡ ታሐይዋ ፡ ለነፍስከ ፡ ወለእለ ፡ ይሰምዑከ ። ወልሂቃነ ፡ ኢታመጕጽ ፡ አላ ፡ ስእል ፡ ኀቢሆሙ ፡ ወናዝዞሙ ፡ ወአስተፍሥሐሙ ፡ ከመ ፡ አብ ። ወለወራዙት ፡ ከመ ፡ አኃዊከ ፡ ወለሰበሳራት ፡ ከመ ፡ እማቲከ ፡ ወለውርዙዋት ፡ ከመ ፡ አኃቲከ ፡ በኵሉ ፡ ንጽሕ ፡ ወክብር ። ወለእጓለ ፡ ማውታ ፡ ወለመበለታት ፡ ግበር ፡ በጽድቅ ፡ ወኢትትወከፍ ፡ ውዴተ ፡ በላዕለ ፡ ቀሲስ ፡ ዘእንበለ ፡ በስምዐ ፡ ፪ቱ ፡ እደው ፡ አው ፡ ፫ቱ ፡ ወገሥፆሙ ፡ ለእለ ፡ ይኤብሱ ፡ በቅድመ ፡ መኳንንት ፡ ከመ ፡ ይፍርሁ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ። ወኢትግበር ፡ ምንተኒ ፡ በአድ

ርን ፡ ይሰምነው ። የሚያስተምረው ፡ ትምህርት ፡ በሰሚዎቹ ፡ ዘንድ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ፍሬ ፡ ያፈራ ፡ ዘንድ ። ድስቅ ፡ ፳፫ ። የሚያስተምረውን ፡ ትምህርት ፡ ሁሉ ፡ እርሱ ፡ እንደሠራው ፡ አስተማረው ፡ ማወቅ ፡ ይገባዋል ። ዘመ፫መረያ ፡ አውጥቶ ፡ አውርዶ ፡ የሚያስተምረውን ፡ ያውቀው ፡ ዘንድ ። እርሱ ፡ የሚያስተምረውን ፡ ካወቀ ፡ የሚሰሙትም ፡ የሚላቸውን ፡ ያውቃሉና ።

፻፲፫ ሁለተኛው ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋር ፡ ሊያደርገው ፡ የሚገባውንና ፡ በርሱ ፡ የሚአዛቸውን ፡ ይናገራል ። ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ ደቀመዝሙሩ ፡ ለነበረው ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ በ፫ኛው ፡ ክፍል ፡ እንዲህ ፡ አለው ። (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፩-፬ ። ፬ ፡ ፲፩-፲፯ ። ፭ ፡ ፩-፲) ። ስለ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በማናቸውም ፡ ሥራ ፡ በምትጸልይበት ፡ ጊዜ ፡ አስቀድመህ ፡ ልመናህን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ታቀርብ ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ እለምንሃለሁ ። በትዕግሥት ፡ በጸጥታ ፡ በአርምሞ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመፍራት ፡ በንጽሕና ፡ ሁነው ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ። እነዚህ ፡ ሥራዎች ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ይድኑ ፡ ዘንድ፡ እውነትንም ፡ ወደማወቅ ፡ ይደርሱ ፡ ዘንድ ፡ ወደሚወድ ፡ ወደ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ ያደርሳሉና ።

፻፲፬ ፰ ። (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፲፩ - ፲፯) ። ለምእመናን ፡ በአነጋገር ፡ በተጋድሎ ፡ በፍቅር ፡ በሃይማኖት ፡ በንጽሕና ፡ አንተ ፡ አብነት ፡ ሁናቸው ። እስክመጣ ፡ ድረስ ፡ መጽሐፍን ፡ በመመልከት ፡ በማስተማር ፡ በምክር ፡ ተጠብቀህ ፡ ኑር ። ትንቢትን ፡ ከመናገር ፡ ጳጳሳትን ፡ በአንብሮተ ፡ እድ ፡ ከመሾም ፡ ጋራ ፡ የሰጠህን ፡ ጸጋ ፡ አታቃል ። በእነርሱ ፡ ጸንተህ ፡ እንድትኖር ፡ እወቅ ። አንተ ይህንን ፡ ብትሠራ ፡ ራስህንና ፡ የሚሰሙህን ፡ ታድናለህ ። ሽማግሎችን ፡ አታሳዝን ። እንደ ፡ አባት ፡ ጸልይላቸው ፡ አረጋጋቸው ፡ አስደስታቸውም ፡ እንጂ ። ለጐበዛዝትም ፡ እንደ ፡ ወንድሞችህ ፡ ለባልቴቶችም ፡ እንደ ፡ እናቶችህ ፡ ለቈነጃጅትም ፡ እንደ ፡ እኅቶችህ ፡ በማናቸውም ፡ ንጽሕናና ፡ ክብር ፡ ሁነህ ፡ ጸልይላቸው ። እናት፡ አባት ፡ ለሌላቸውና ፡ ባሎቻቸው ፡ ለሞቱባቸው ፡ በእውነት ፡ ሥራ ። በቄስ ፡ ላይ ፡ ነገር ፡ ሥራን ፡ አትስማ ። ሁለት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ ካልመሰከሩበት ፡ በተር ፡ ነገረ ፡ ሠሪን ፡

ልዎ ፡ ጎጸ ፡ ወኢታፍጥን ፡ እንብሮ ፡ እዴከ ፡
ላዕለ ፡ ፩ዱሂ ። ወኢትሳተፍ ፡ በዘንቱ ፡ ኃጢ
አቱ ፡ ካልእከ ።

፪፻፳ ዘኒተ ፡ ወእለሂ ፡ እማስኑ ፡ ነፍሳቲሆሙ ፡ ወሰ
ሐቱ ፡ እምፍኖተ ፡ ርትዕ ፡ ወይመስሎሙ ፡
ከመ ፡ ፍርሃተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተማይጦ ፡ ወረ
ባኅ ፡ ይእቲ ፡ ረኀቅ ፡ እምኔሆሙ ። ወለነሰ ፡
ረባኀቲነ ፡ ዐባይ ፡ ወይእቲ ፡ ፍርሃተ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ በአእክሎ ፡ ሲሳይ ። እስመ ፡ እልቦ ፡
ዘአምጻእነ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ምንተኒ ። ወናሁ ፡
ነአምር ፡ ንሕነ ፡ ከመ ፡ አልቦ ፡ ዘንነሥእ ፡ እም
ኔሃ ፡ ካዕበ ፡ ምንተኒ ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ይደሉ
ዘየአክለነ ፡ እምኔሃ ፡ ንንሣእ ፡ ሲሳየ ፡ ወልብሰ ።
እለሰ ፡ ያፈቅሩ ፡ ንዋየ ፡ ወይፈቅዱ ፡ ከመ ፡ ይብ
ዐሉ ፡ ይወድቁ ፡ ውስተ ፡ መንሱት ፡ ወመሥገ
ርት ፡ ወፍትወት ፡ ብዝኀት ፡ ዘታስሕት ፡ ወታ
ስጥም ፡ ሰብእ ፡ ውስተ ፡ ሙስና ፡ ወሐጕል ።
እስመ ፡ ሥርወ ፡ ለኵሉ ፡ እከይ ፡ አፍቅሮ ፡
ንዋይ ። ወናሁ ፡ ጽሕቁ ፡ ዘንተ ፡ ብዙኃን ፡
ሰብእ ፡ ወስሕቱ ፡ እምሃይማኖት ፡ ወአብኡ ፡
ነፍሳቲሆሙ ፡ ውስተ ፡ ምንዳቤ ፡ ብዙኅ ። ወአን
ተሰ ፡ አ ፡ ብእሴ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጕየይ ፡ እም
ዝንቱ ፡ ግብር ፡ ወዴግን ፡ ኀበ ፡ ኅሢሠ ፡ ጽድቅ ፡
ወርትዕ ፡ ወውስተ ፡ አሠረ ፡ ተይማኖት ፡ ወተ
ፋቀሮ ፡ ወውስተ ፡ አሠረ ፡ ትዕግሥት ፡ ወትሕ
ትና ። ወተጋደል ፡ በእንተ ፡ ሃይማኖት ፡ ርት
ዕት ፡ ወሠናይት ፡ ወትረክብ ፡ ሕይወተ ፡ ዘለ
ዓለም ፡ እንተ ፡ ላቲ ፡ ተጸዋዕከ ። ወአዝዞሙ ፡
ለአብዕልተ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ከመ ፡ ኢይት
ዐበዩ ፡ በአልባቢሆሙ ፡ ወኢይትወከሉ ፡
በብዕሎሙ ፡ ዘአልቦ ፡ ተወክሎ ፡ በላዕሌሁ ።
አላ ፡ ይትአመኑ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡
ዘወሀበነ ፡ ኵሎ ፡ በብዝኀ ፡ ብዕሉ ፡ ለዕረፍተ ፡
ዚአነ ። ወከመ ፡ ይብዐሉ ፡ በምግባረ ፡ ሠናይ ፡
ወያፍጥኑ ፡ ለውሂብ ፡ በአዕርዮ ፡ ወያንብሩ ፡
ለነፍስሙ ፡ መሠረተ ፡ ሠናየ ፡ ለግብር ፡ ዘይመ
ጽእ ፡ ከመ ፡ ይርከቡ ፡ ሕይወተ ፡ ዘበአማን ።
አ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ተዓቀብ ፡ ዘአማኅፀንኩከ ፡
ወጕየይ ፡ እምሰሚዐ ፡ ከንቱ ፡ ወኢመጋድ
ምተ ፡ ዓለም ፡ ሐሳዊ ። እስመ ፡ እለ ፡ የኀሥሡ ፡



አትስማ ። የበደሉትን ፡ በሊቃውንት ፡ ፊት ፡
ገሥጻቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ይፈሩ ፡ ዘንድ ።
ፊትን ፡ አይቶ ፡ በማድላት ፡ ምንም ፡ ምን ፡ አት
ሥራ ። ማንንም ፡ ፈጥነህ ፡ በእንብርተ ፡ እድ ፡
አትሹም ። በዚህ ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ ኃጢአት ፡
አትካፈል ።

፪፻፳ በ፮ኛውም ፡ ክፍል ፡ እንዲህ ፡ አለ ። (፩ጢሞ ፡
፮ ፡ ፫-፳፩) ። ሰውነታቸውን ፡ በኃጢአት ፡ ያጠ
ፉትንና ፡ ከቀናው ፡ መንገድ ፡ የራቁትን ፡ እግ
ዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ ንግድና ፡ ጥቅም ፡ የሚ
መስላቸውን ፡ ሰዎች ፡ ተለያቸው ። እኛስ ፡
ታላቁ ፡ ጥቅማችን ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍ
ራት ፡ ነው ። የዕለት ፡ ምግባችንን ፡ ማግኘታ
ችን ፡ ይበቃናል ። ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ ያመጣነው
ነገር ፡ ምንም ፡ የለምና ። እነሆ ፡ እኛ ፡ ሁለተኛ
ከርሷ ፡ የምንወስደው ፡ እንደሌለን ፡ እናውቃ
ለን ። ስለዚህ ፡ ከእርሷ ፡ ምግብና ፡ ልብስ ፡
እንወስድ ፡ ዘንድ ፡ ይበቃናል ። ገንዘብን ፡ የሚ
ወዱ ፡ ለመበልጠግም ፡ የሚሹ ፡ ግን ፡ ወደ ፡
ፈተና ፡ ወደ ፡ ወጥመድ ፡ ሰውን ፡ በፍጹም ፡
ጥፋት ፡ በምታስጥምና ፡ በምታስት ፡ ብዙ ፡
በሆነች ፡ ምኞት ፡ ይወድቃሉ ። የክፋ ፡ ሥራ ፡
ሁሉ ፡ ምንጩ ፡ ገንዘብን ፡ መውደድ ፡ ነውና ።
እነሆ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ይህንን ፡ ተመኝተው ፡
ከሃይማኖታቸው ፡ ወጡ ። ሰውነታቸውንም ፡
በብዙ ፡ ችግር ፡ ውስጥ ፡ ጣሉ ። አንተ ፡ ግን ፡
የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ሆይ ፡ ከዚህ ፡ ሥራ ፡
ራቅ ። እውነትን ፡ መፈለግን ፡ ተከተል ፡ የትዕ
ግሥትንና ፡ የትህትናን ፡ ፈለግ ፡ ተከተል ። ስለ፡
ቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ ተጋደል ። የተጠራኸላትን ፡
የዘላለም ፡ ሕይወት ፡ ታገኛለህ ። ለእኛ ፡ ዕረ
ፍት ፡ በብዙ ፡ ስጦታው ፡ ሁሉን ፡ በሰጠን ፡ በእ
ግዚአብሔር ፡ ይታመኑ ፡ እንጂ ፡ ሊታመኑበት ፡
በማይገባ ፡ ሀብታቸው ፡ እንዳይታመኑ ፡ በል
ባቸው ፡ እንዳይታበዩ ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ባለጠ
ጎች ፡ እዘዛቸው ። በበጎ ፡ ምግባር ፡ ይበለጽጉ ፡
ዘንድ ፡ እውነተኛውንም ፡ ሕይወት ፡ ያገኙ ፡
ዘንድ ፡ ለሚመጣው ፡ ሥራ ፡ መልካም ፡ መሠ
ረት ፡ ለነፍሳቸው ፡ ያኖሩ ፡ ዘንድ ፡ እዘዛቸው ።
ጢሞቴዎስ ፡ ሆይ ፡ አደራ ፡ ያልኩህን ፡ ጠብቅ።
ከንቱን ፡ ነገር ፡ ከመስማት ፡ ሐሰተኛ ፡ ከሆነ
ውም ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ተረት ፡ ራቅ ። ይህን ፡
የሚፈልጉ ፡ ሁሉ ፡ ከሃይማኖት ፡ እነሆ ፡ ወጥተ

ዘንተ ፡ ናሁ ፡ ስሒቱ ፡ እምሃይማኖት ፡ ወጸጋ ፡ ምስሌከ ፡ አሜን ።

ዋልና ። ጸጋ ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ ትሁን ፡ አሜን ።

፻፲፮ ድስቅ ፡ ፬ቱ ፡ ጸሐቅ ፡ ሊቃለ ፡ ትምህርት ፡ አ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወለእመ ፡ ኮንከ ፡ ትክል ፡ ተር ጕሞ ፡ እምነ ፡ ኵሉ ፡ መጻሕፍት ፡ ቃላተ ፡ አጽ ግቦሙ ፡ ለሕዝብከ ፡ ወአብርሀ ፡ ሎሙ ፡ እምነ ፡ ብርሃነ ፡ሕጊጋቲከ ፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ በዝንቱ ፡ እብዕልተ ፡ በብዝኀ ፡ ትምህርትከ ።

፻፲፮ ድስቅ ፡ ፬ ። ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ሆይ ፡ ለማስተማር ፡ ትጋ ። መጻሕፍትን ፡ ሁሉ ፡ ለመተርጐም ፡ ብትችል ፡ ሕዝብህን ፡ ትምህርት ፡ አጥግባ ቸው ። በብዙ ፡ ትምህርተ ፡ ባለጠጎች ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ። ከሕጎችህ ፡ ብርሃን ፡ አብራላቸው ።

፻፲፯ ወይደሉ ፡ ለክሙ ፡ አ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ከመ ፡ ትኩኑ ፡ ሰብአ ፡ ዓይነ ፡ ለሕዝብ ። እስመ ፡ እስ ይንቲሁ ፡ እንትሙ ፡ ለክርስቶስ ። ወእግዚአብ ሔር ፡ ይቤ ፡ በአፈ ፡ ሕዝቅኤል ፡ ነቢይ ፡ በእን ቲአክሙ ፡ አ ፡ ወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ረሰይኩከ ፡ ሰብአ ፡ ዓይነ ፡ ለዝንቱ ፡ ሕዝብ ፡ ትስማዕ ፡ እምኔየ ፡ ነገረ ፡ ወትሰብኮ ፡ ወትሰቀ ቦሙ ፡ ቦቱ ፡ እመንገለ ፡ ገጽየ ፡ እምነቢየ ። እስመ ፡ ለእመ ፡ ኢነገርኮ ፡ ለኃጥእ ፡ ከመ ፡ ይትዐቀብ ፡ እምነ ፡ ኃጢአቱ ። ወውእቱ ፡ ኃጥእ ሶበ ፡ ሞተ ፡ በኃጢአቱ ፡ ወደሞ ፡ እት ኀሠሥ ፡ እምእዴከ ። ወለእመስ ፡ አቅደምከ ፡ ወአመርኮ ፡ ለኃጥእ ፡ ወነገርኮ ፡ ከመ ፡ ይትገ ኃሥ ፡ እምእከዩ ፡ ወኢተማኅፀ ፡ እምኔሁ ፡ ውእቱ ፡ ኃጥእ ፡ ወሞተ በኃጢአቱ ፡ ወአንተ ፡ አድኀንከ ፡ ነፍሰከ ። ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ መሀር ዎሙ ፡ ለእለ ፡ የሐውሩ ፡ ዘእንበለ ፡ እእምሮ ፡ ወለእለ ፡ ተምሀሩ ፡ አጽንዕዎሙ ፡ ወሚጥዎሙ፡ ለስሑታን ፡ ወንግርዎሙ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ በእ ንተ ፡ ስሕተቶሙ ።

፻፲፯ ኤጲስቆጶሳት ፡ ሆይ ፡ ለሕዝቡ ፡ ጉበኞች ፡ ትሆ ኑ ፡ ዘንድ ፡ ይገባችኋል ። የክርስቶስ ፡ ዓይኖቹ፡ እናንተ ፡ ናችሁና ። እግዚአብሔርም ፡ ስለእና ንተ ፡ በነቢዩ ፡ በሕዝቅኤል ፡ አፍ ፡ እንዲህ ፡ አለ ። (ሕዝ ፡ ፫ ፡ ፲፯ - ፳፩) ። "የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፡ ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ጉበኛ ፡ አደረግሁህ ። ከእኔ ፡ ነገር ፡ ሰምተህ ፡ እንድታስተምር ፡ እን ደኔ ፡ እንደራሴ ፡ ሆነህ ፡ ትጠብቃቸው ፡ ዘንድ ፡ ኃጥኡ ፡ ከኃጢአቱ ፡ ይጠበቅ ፡ ዘንድ ፡ ባትነግ ረው ፡ ይህም ፡ በኃጢአቱ ፡ ሳለ ፡ ቢሞት ፡ ደሙን ፡ ከአንተ ፡ እፈልጋለሁ ። አስቀድመህ ፡ ግን ፡ ከኃጢአቱ ፡ እንዲመለስ ፡ ብትነግረው ፡ ይህ ፡ ከኃጢአቱ ፡ ባይመለስ ፡ በኃጢአቱም ፡ ቢሞት ፡ አንተ ፡ ራስህን ፡ አዳንህ" ። ስለዚ ህም ፡ ያለ ፡ እውቀት ፡ የሚኖሩትን ፡ አስተምሯ ቸው ። የተማሩትን ፡ አጽኗቸው ። የተሳሳቱት ንም ፡ መልሷቸው ። በየጊዜውም ፡ ስለ ፡ ስሕተ ታቸው ፡ ንገሯቸው ።

፻፲፰ አቅም ፡ ነፍሰከ ፡ በንጽሕ ፡ አ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በኵሉ ፡ ምግባርከ ። ወእእምር ፡ መንገሥ ፡ ሢመ ትከ ፡ እስመ ፡ አንተ ፡ እምሳለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በኀበ ፡ ሕዝብ ፡ በሢመትከ ፡ ወኮንከ ፡ ርእሰ ፡ ለሰብእ ፡ ወለኵሎሙ ፡ ነገሥት ፡ ወመኳንንት ፡ ወካህናት ፡ ወለአበው ፡ ወለውሉዶሙ ፡ እለ ፡ ተምሀሩ ። ወለኵሎሙ ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡ ታሕተ ፡ ትእዛዝከ ። ንበር ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ክርስቲያንከ፡ ወሰብኮ ፡ ቢቃል ፡ እስመ ፡ ለከ ፡ ሥልጣን ፡ ከመ ፡ ትኰንን ፡ ኃጥአነ ። እስመ ፡ ለክሙ ፡ ይቤ ፡ እለ ፡ ተእስርዎሙ ፡ በምድር ፡ ይኩኑ ፡ እሱራነ ፡ በሰማያት ፡ ወእለሂ ፡ ትፈትሕዎሙ ፡ በምድር ፡ ይኩኑ ፡ ፍቱሓነ ፡ በሰማያት ። ኰንን፡ በሥልጣን በእምሳለ ፡ እግዚአብሔር ። ወለ ዘነስሐ ፡ ተወከፎ ፡ ኀቤከ ፡ እስመ ፡ እግዚአብ

፻፲፰ ኤጲስቆጶስ ፡ ሆይ ፡ በሥራው ፡ ሁሉ ፡ ራስህን ፡ በንጽሕና ፡ አጽና ። የሹመትህንም ፡ መንገሻ ፡ እወቅ ። በሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ በሹመትህ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነህና ። ለሕዝቡ ፡ ለነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ ለመኳንንት ፡ ለካህናት ፡ ለአባቶችና ፡ ለተማሩት ፡ ልጆቻቸው ፡ ከትእዛዝህ ፡ በታች ፡ ላሉት ፡ ሁሉ ፡ አለቃ ፡ ሁነሃልና ። በቤተ ፡ ክርስ ቲያንህ ፡ ተቀመጥ ። በቃልህም ፡ አስተምር ። በኃጥአን ፡ ትፈርድ ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣን ፡ አለ ህና ። በምድር ፡ ያሰራችኋቸው ፡ በሰማይ ፡ የታ ሰሩ ፡ ይሆናሉ ፡ በምድርም ፡ የፈታችኋቸው ፡ በሰማይ ፡ የተፈቱ ፡ ይሆናሉ ፡ (ዮሐ ፡ ፳ ፳፫) ። ብሎ ፡ ለናንተ ፡ ተናግሯልና ። በእግዚአብሔር እምሳል ፡ በሥልጣንህ ፡ ፍረድ ። ንስሓ ፡ የገባ ውን ፡ ሰው ፡ወደአንተ ፡ ተቀበለው ። እግዚአ

ሔር ፡ አምላከ ፡ ምሕረት ፡ ውእቱ ።
፻፲፱ ንሥኦ ፡ ለዘይኤብስ ፡ ወኢትስድዶ ፡ ለዘይኔስሕ ። አስተሐምም ፡ አ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ለመድኃኒተ ፡ ኩሉ ፡ ሰብእ ፡ ለለ፩ ፡ እስመ ፡ ለከሙ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ ዑቁ ፡ ኢታስተሐቅርዎ ፡ ለ፩ ፡ እምእሉ ፡ ንኡሳን ወእእምር ፡ በዝንቱ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ይእዜ ፡ ይትኄሠሥ ፡ እምኔከ ፡ ብዙኀ ፡ እውሥኦ ፡ ፈድፋደ ፡ ለዘአማኅፀንዎ ፡ ብዙኀ ፡ ይትኄሠሥዎ ፡ ብዙኀ ።
፻፳ ሀሉ ፡ አንተ ፡ እንበለ ፡ ሐሜት ፡ ከመ ፡ ኢይትሀየድ ፡ በእንቲአከ ፡ ፩ዱሂ ፡ ወሕዝባዊ ፡ ያስተሐምም ፡ በነፍሱ ፡ እንተሰ ፡ ያርከ ፡ ያረ ፡ ከቡድ ። ጽሑፍ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቤሎ ፡ ለሙሴ አንተ ፡ ወአሮን ፡ ትፀውሩ ፡ አበሳሆሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ተዓዋርያን ። መሀሮሙ ፡ ለእለ ፡ ይትሄየዩ ፡ ወአእምር ፡ ከመ ፡ ለከ ፡ ሰሚት ፡ ዐቢይ ፡ ለእመ ፡ ገበርከ ፡ ዘንተ ፡ በከመ ፡ ብከ ፡ ኵነኔ ፡ ሀቢይ ፡ ለእመ ፡ ተሀከይከ ፡ በእንቲአሁ ።
፻፳፩ ወሶበ ፡ መጽአ ፡ ኀቢከ ፡ ዘሀለወ ፡ ቦቱ ፡ ዐቢይ ፡ አበሳ ፡ ኢትትኀየይ ፡ ኪያሁ ። ይቤ ፡ ሕዝቅኤል ፡ ነቢይ ፡ በእንተ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘይትሄየይ ፡ እንበይነ ፡ ሕዝቡ ፡ አሌ ፡ ሎሙ ፡ ለኖሎተ ፡ እስራኤል ፡ እለ ፡ ኀደጉ ፡ አባግዒሆሙ ፡ ዘይርዕዩ ፡ ለለ፩ ፡ እኩኑ ፡ አንትሙ ፡ ኖሎት ፡ ዘትርዕዩ ፡ አባግዐ ። ወአንትሙ ፡ ለሐሊብ ፡ ትሰትዩዎ ፡ ወለፀምር ፡ ዘትለብስዎ ፡ ወለሥጋዘእኒ ፡ ሰቡሕ ፡ ዘትጠብሕዎ ፡ ወአባግዐየሰ ፡ ኢትርዕዩ ፡ ወለዘደክመ ፡ ኢታጸንዕዎ ፡ ወለዘተሰብረ ፡ ኢትፌውስዎ ፡ ወለዘተገድፈ ፡ ኢተኀሥሥዎ ፡ ወለዘተሐጒለ ፡ ኢትረክብዎ ፡ ወኢትሚሀርዎሙ ፡ ትምህርተ ፡ በውስየተ ፡ ልብ ፡ ዳዕሙ ፡ በስላቅ ። ወተዘርዉ ፡ አባግዕየ ፡ በእንተ ፡ ዘአልቦሙ ፡ ኖላዊ ፡ ወኮኑ ፡ መብልዐ ፡ ለአናብስተ ፡ ገዳም ። ወይቤ ፡ ካዕበ ፡ አንሰ ፡ አፈትሕ ፡ ማእከለ ፡ አባግዕ ፡ ወኖሎት ፡ ወማእከለ ፡ በግዕ ፡ ወበሐኵ ፡
፻፳፪ ለዘኒ ፡ አበሰ ፡ አ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወአውፃእኮ ፡ በግዘት ፡ ኢትኅድጎ ፡ አፍኦ ፡ አላ ፡ ሚጦ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ። ወለዘተገድፈ ፡ ኅሥሦ ፡ ወለዘኢይሴፎ ፡ መድኀኒተ ፡ በእንተ ፡ ብዝኀ ፡ ኃጣውኢሁ ፡ ኢትኅድጎ ፡ ይትሐጐል ፡ በኵሉ ።

ብሔር ፡ የምሕረት ፡ አምላክ ፡ ነውና ።
፻፲፱ የበደለውን ፡ ምከረው ፡ ንስሐ ፡ የገባውንም ፡ አታባረው ። ኤጲስቆጶስ ፡ ሆይ ፡ እየንዳንዱ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ለማዳን ፡ ትጋ ። ጌታችን ፡ ለናንተ ፡ ከታናናሾቹ ፡ አንዱን ፡ አታቃልሉ ፡ ብሏልና ፡ (ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፲) ። በዚህ ፡ ካንተ ፡ ብዙ ፡ እንደሚፈለግብህ ፡ እወቅ ። ብዙ ፡ አደራ ፡ ያሉትን ፡ ብዙ ፡ ይፈልጉበታልና ። (ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፵፰) ።
፻፳ አንዱ ፡ ስንኳ ፡ በአንተ ፡ እንዳይሰናከል ፡ ያለ ሐሜት ፡ ኑር ። ሕዝባዊ ፡ ለራሱ ፡ ያስባል ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ከባድ ፡ ሸክም ፡ ተሸክመሃል ። እግዚአብሔር ፡ ለሙሴ ፡ "አንተና ፡ አሮን ፡ የሕግ ፡ አፍራሾች ፡ የሕዝቡን ፡ በደል ፡ ትሸከማላችሁ ፡ አለው ። (ዘኍ ፡ ፲፰ ፡ ፩-፪) ። የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ አለ ። ቸልተኞችን ፡ አስተምራቸው ። ቸል ፡ ብትል ፡ ስለነሱ ፡ ትልቅ ፡ ቅጣት ፡ እንዳለብህ ፡ ይህንን ፡ ብታደርግ ፡ ታላቅ ፡ ዋጋ ፡ እንዳለብህ ፡ እወቅ ።
፻፳፩ ትልቅ ፡ በደል ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ ወዳንተ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ቸል ፡ አትበለው ። ነቢዩ ፡ ሕዝቅኤል ፡ ሕዝቡን ፡ ቸል ፡ ስለሚል ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እንዲህ ፡ አለ ። (ሕዝ ፡ ፴፬ ፡ ፪ - ፭) ። እየንዳንዱ ፡ የሚጠብቋቸውን ፡ በጎች ፡ ለተዉ ፡ ለእስራኤል ፡ ጠባቂዎች ፡ ወዮላቸው ። በጎችን ፡ የምትጠብቁ ፡ እረኞች ፡ እናንተ ፡ አይደላችሁምን ፡ ወተቱን ፡ የምትጠጡት ፡ ጠጕሩን ፡ የምትለብሱት ፡ የሰባውን ፡ ፍሪዳ ፡ የምታርዱት ፡ እናንተ ፡ አይደላችሁምን ። በጎችን ፡ አትጠብቁም ፡ የደከመውን ፡ አታጸኑትም ፡ የተሰበረውን ፡ አትጠግኑትም ፡ የጠፋውን ፡ አታገኙትም ። በኃለ ፡ መንፈስ ፡ አታስተምሩዋቸውም ፡ በፌዝ ፡ ነው ፡ እንጂ ። በጎቼ ፡ ጠባቂ ፡ ስለሌላቸው ፡ ተበተኑ ፡ ለዱር ፡ አንበሶችም ፡ ምግብ ፡ ሆኑ" ፡ አለ ። ዳግመኛም ፡ በበጎችና ፡ በእረኞች ፡ መካከል ፡ በአውራውና ፡ በመንጋውም ፡ መካከል ፡ እፈርዳለሁ ፡ አለ ። (ሕዝ ፡ ፴፬ ፡ ፲፯) ።
፻፳፪ ኤጲስቆጶስ ፡ ሆይ ፡ የበደለውን ፡ አውግዘህ ፡ ብትለየው ፡ በውጭ ፡ አትተወው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መልሰው ፡ እንጂ ። የጠፋውንም ፡ ፈልግ ። ስለ ፡ ኃጢአቱ ፡ ብዛት ፡ እድናለሁ ፡ ብሎ ፡ ተስፋ ፡ የማያደርገውን ፡ በሁሉ ፡ ጠፍቶ ፡

ወከመዝ ፡ ይደልዎ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ይፁር ፡ ኃጢአተ ፡ ኃጥእ ፡ ሳሌስ ፡ ነፍሱ ፡ ወይረሲ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ዘአበሰ ፡ ውእቱ ፡ ፈድፋደ ፡ ወይበሎ ፡ ለዘአበሰ ፡ ተመየጥ ፡ አንተ ፡ ወአነ ፡ እትዌከፍ ፡ ሞተ ፡ ዘየንቲከ ፡ እምሳለ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘሞተ ፡ በእንቲአየ ፡ ወበእንተ ፡ ኵሎሙ ። ወይቤ ፡ “ አነ ፡ ኖላዊ ፡ ኄር ፡ ኖላዊስ ፡ ኄር ፡ ይሜጡ ፡ ነፍሶ ፡ ህየንተ ፡ አባግዒሁ ፡ ወንሳብስ ፡ ዘኢኮነ ፡ ኖላዌ ወኢኮና ፡ አባግዕ ፡ ዘዚአሁ ፡ ሶበ ፡ ርእየ ፡ እንዘ ፡ ይመጽእ ፡ ተኵላ ፡ ሀውእቱ ፡ ዲያብሎስ ፡ የኅድጎን ፡ ለአባግዕ ፡ ወይጐይይ ፡ ወይመሥጦን ፡ ተኵላ ፡ ለእሉ ፡ አባግዕ ።

፻፳፫ ዐቃቢ ፡ አባግዕ ፡ ኀሠሠ ፡ በግዐ ፡ ዘተገድፈ ፡ ከመ ፡ እግዚእነ ፡ ይቤ ፡ ውእቱ ፡ የኅድግ ፡ ፺ ወ፱ተ ፡ ውስተ ፡ ደብር ፡ ወየሐውር ፡ ይኅሥሥ ፡ ዘተገድፈ ፡ ወሶበ ፡ ረከቦ ፡ ይፀውሮ ፡ ዲበ ፡ መትከፍቱ ፡ ወያበውእ ፡ ኀበ ፡ መርዔት ፡ እንዘ ፡ ይትፌሣሕ ፡ ውእቱ ፡ በእንቲአሁ ።

፻፳፬ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ድውየ ፡ በኃጢአት ፡ የኅሥሥ ፡ ዐቃቢ ፡ ሥራይ ፡ ልብወ ፡ ዘይትራድኦ ፡ በእንተ ፡ ሕማሙ ፡ ወነዋ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ” ፡ እኮ ፡ ጥዑያን ፡ ዘየኅሥሥዎ ፡ ለዐቃቢ ፡ ሥራይ ፡ ዳእሙ ፡ ድውያን ፡ ወወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ሶበ ፡ መጽአ ፡ እንዘ ፡ ውእቱ ፡ ዐቃቢ ፡ ሥራይ ፡ አድኅነ ፡ ወፈወሰ ፡ ድውያነ ” ።

፻፳፭ ወኢታፍቅር ፡ መስተዋድያነ ፡ ወኢስሱዓነ ። ወለእመ ፡ ርኢከ ፡ ለኃጥእ ፡ ገሃደ ፡ በበንስቲት ፡ ወኢታፍጥን ፡ ሰዲዶቶ ፡ ወእዝዞሙ ፡ ለዲያቆናት ፡ ይርከብዎ ፡ አፍአ ፡ ወይኅትውዎ ፡ ወያግብእዎ ፡ ወይጸልዩ ፡ በእንቲአሁ ፡ እሚሃ ፡ ሥራዕ ፡ ሎቱ ፡ ጾመ ፡ በእንተ ፡ ኃጢአቱ ፡ በአምጣነ ፡ ክሂሎቱ ፡ አሐደ ፡ ወ፪ተ ፡ ሱባዔያተ ፡ አው ፡ ሠለስተ ፡ አው ፡ አርባዕተ ፡ አው ፡ ሐምስተ ፡ አው ፡ ስድስተ ። ወመሀሮ ፡ ከመ ፡ ይትገሠጽ ፡ በከመ ፡ ይደሉ ፡ ለሥርየተ ፡ ኃጢአቱ ፡ ወአክብሮ ፡ ወመሀሮ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ትሑተ ፡ ወየዋሀ ፡ በርእሱ ።

፻፳፮ ዘንቱ ፡ ወይደሉ ፡ ለኵሉ ፡ ኦ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ከመ ፡ ትረስይዎ ፡ ለኵሉ ፡ አርአያ ፡ ለመድኃኒነ ፡ ወንጉሥነ ፡ ወአምላክነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስ



ይቀር ፡ ሀንደ ፡ አትተወው ። እንዲሁም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ የኃጥኡን ፡ ኃጢአት ፡ ሊሸከም ፡ ይገባዋል ። እርሱም ፡ ፈጽሞ ፡ እንደበደለ ፡ ያድርግለት ። የበደለውንም ፡ “ አንተ ፡ ተመለስ ፡ እኔም ፡ ስለእኛና ፡ ስለ ፡ ሁሉ ፡ በሞተው ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አምሳል ፡ ስለአንተ ፡ ሞትን ፡ እቀበላለሁ ” ይበለው ። “ እኔ ፡ ቸር ፡ ጠባቂ ፡ ነኝ ፡ ቸር ፡ ጠባቂ ፡ ስለ ፡ በጎቹ ፡ ሰውነቱን ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣል ፡ ጠባቂ ፡ ያልሆነ ፡ በጎቹም ፡ የእርሱ ፡ ያይደሉ ፡ ደመወዝተኛ ፡ ግን ፡ ይኸውም ፡ ዲያብሎስ ፡ ነው ፡ ተኵላ ፡ ሲመጣ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ በጎቹን ፡ ትቶ ፡ ይሸሻል ፡ በጎቹን ፡ ተኵላ ፡ ይነጥቃቸዋል ።” ይላል (ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፲፩ - ፲፪) ።

፻፳፫ የበጎች ፡ ጠባቂ ፡ ሆይ ፡ የጠፋውን ፡ በግ ፡ ፈልግ ፡ ዘጠና ፡ ዘጠኙን ፡ በተራራ ፡ ላይ ፡ ትቶ ፡ የጠፋውን ፡ ሊፈልግ ፡ ይሄዳል ፡ ባገኘውም ፡ ጊዜ ፡ በትከሻው ፡ ተሸክሞ ፡ እርሱ ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ ደስ ፡ እያለው ፡ ወደ ፡ መንጋው ፡ ያገባዋል ፡ ብሎ ፡ ጌታችን ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ (ሉቃ ፡ ፲፭ ፡ ፬ - ፯) ።

፻፳፬ በኃጢአት ፡ የታመመ ፡ ቢሆን ፡ ስለ ፡ ሕማሙ ፡ የሚረዳው ፡ አዋቂ ፡ ሐኪም ፡ ይፈልጋል ። እነሆ ፡ ጌታችን ፡ ሐኪምን ፡ የሚፈልጉት ፡ ጤነኞች ፡ አይደሉም ። በሽተኞች ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ (ማቴ ፡ ፱ ፡ ፲፪ - ፲፫) ። አለ ። የሰው ፡ ልጅ ፡ ሐኪም ፡ ሆኖ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ድውዮችን ፡ ፈጽሞ ፡ አዳነ ።

፻፳፭ ነገረ ፡ ሠሪዎችንና ፡ ስስታሞችን ፡ አትውደድ ። ኃጢአተኛውን ፡ ብታገኘው ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ ምከረው ። ፈጥነህ ፡ አትለየው ። ዲያቆናትም ፡ በውጭ ፡ አግኝተው ፡ አባብለው ፡ እንዲመልሱት ፡ ስለርሱም ፡ እንዲጸልዩ ፡ እዘዛቸው ። ያንጊዜ ፡ በችሎታው ፡ መጠን ፡ ጾም ፡ ሥራለት ። አንድና ፡ ሁለት ፡ ሱባዔ ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ ወይም ፡ ፬ ፡ ወይም ፡ ፭ ፡ ወይም ፡ ፮ ፡ ሱባዔ ፡ ሥራለት ። ኃጢአቱን ፡ ለማስተሥረይ ፡ በሚገባ ፡ እንዲገሠጽ ፡ አስተምረው አክብረው ። በራሱ ፡ ትሑት ፡ የዋህ ፡ እንዲሆን አስተምረው ።

፻፳፮ ድስቅ ፡ ፭ ። ኤጲስቆጶሳት ፡ ሆይ ፡ መድኃኒታችንን ፡ ንጉሣችንን ፡ አምላካችንን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ አብነት ፡ ልታደርጉት ፡ ይገባች

ቶስ ። ወትኩንዎ ፡ ስብአ ፡ ዓይን ፡ ወተመስሉ ፡
ኪያሁ ፡ ከመ ፡ ትኩኑ ፡ መሐሪያነ ፡ ወገባርያነ ፡
ሰላም ። ወእኩ ፡ ድንጹዋነ ፡ ወእሰቡያነ ፡ ወእ
መደልዋነ ፡ ገጽ ፡ ወእዝንጉዓነ ፡ ወእበላስያነ ፡
ወእስታይያነ ፡ ዘእንበለ ፡ ዓቅም ። ወእታስ
ትቱ ፡ ሀብታተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዳሰሙ ፡ ተወ
ከፍዎ ፡ እስመ ፡ አንትሙ ፡ ናሁ ፡ ኮንክሙ ፡ መን
ብተ ፡ ኄራነ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ ሎቱ ፡
ታገብኡ ፡ ምግብና ፡ ወሥርዓተ ፡ ዘወሀበክሙ ።

፻፳፯ ወያኩን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘይኀሥእ ፡ እምነ ፡ መብ
ልዕ ፡ ወልብስ ፡ በአምሣነ ፡ ዘየአክሎ ፡ ዘይ
ደሉ ፡ ለመፍቅድ ፡ በንጽሕ ፡ እስመ ፡ ይደልዎ ፡
ሀሰቡ ፡ ለዘይትቀነይ ፡ ወኢየሥኒ ፡ አልባሲሁ ።
ዳሰሙ ፡ ይንሣእ ፡ ዘይትፈቀድ ፡ ለከዲነ ፡
ሥጋሁ ፡ ባሕቲቱ ፡ አኮ ፡ ካልአ ፡ ሥርጋዌ ፡
ዘይሜኒ ።

፻፳፰ አንትሙ ፡ ይእዜ ፡ ካህናት ፡ በቅድመ ፡ ሕዝብ
ክሙ ። ወአንትሙሰ ፡ ሌዋውያን ፡ ላእካነ ፡
ደብተራ ፡ ቅድስት ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ቤተ ፡ ክር
ስቲያን ፡ ጉባኤ ፡ ቅድስት ። አንትሙ ፡ አበዊ
ሆሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ቤታሕቱ ፡ እደዊክሙ ፡ አን
ትሙ ፡ አርእስት ፡ በላዕሌሆሙ ፡ ለሊቃናት ፡
ወንገሥታት ፡ ወመገብት ፡ አንትሙ ፡ በሬቅ
ያን ፡ ማእከለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወሰብእ ። ወም
እመናኒሆሙ ፡ ወመራድያን ፡ ኃጢኡአ ፡ ነፍሉ ፡
ወእውማእያን ፡ በእንቲአሆሙ ። ወለክሙ ፡
ካሰበ ፡ ሰሜት ፡ ወቢይ ፡ እምነበ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ወከብር ፡ ዘኢይትነገር ፡ ስብሐተ ፡
ዚአሁ ፡ አንትሙ ፡ ዘትትለአኩ ፡ ለቤተ ፡ ክርስ
ቲያን ፡ ቅድስት ፡ ሥናየ ፡ ተልእኮ ። ወበከመ ፡
አንትሙ ፡ ያርክሙ ፡ ኃጢአተ ፡ ነፍሉ ፡ ለለ
አሐዱ ፡ ከማሁ ፡ ካሰበ ፡ አንትሙ ፡ ትንሥኡ ፡
መብልዐክሙ ፡ ወልብስክሙ ፡ ወመፍቅዳቲ
ክሙ ፡ እምነ ፡ ነፍሉ ፡ ለለአሐዱ ።

፻፳፱ ድስቅ ፡ ፴ ፡ ኩኑ ፡ ወቢባነ ፡ በአምሳለ ፡ ነሀብተ ፡
ብሩር ፡ ከማሁ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ኤጲ
ቆጶስ ፡ ለሰብእ ፡ ዘየቀርቦሙ ፡ ኀቤሁ ፡ ለእለ ፡
ቦሙ ፡ ተምያን ፡ ወአበሳ ፡ ይፈውሶሙ ። ወለ
ኢመ ፡ ኮነ ፡ ደዌሆሙ ፡ አልቦቱ ፡ ፈውስ ፡ የርን
ቆሙ ፡ እምኔሁ ፡ ወኢያርንቆሙ ፡ እምኔሁ ፡
አርንቶተ ፡ ፍጹመ ፡ በመተር ። ወኢይትአመን ፡
መንፈ ፡ አሐዱ ፡ ላዕለ ፡ ሥርዓተ ፡ ምግብናሁ ።



ኋል ። ጉበኞችም ፡ ልትሆኑ ፡ ይገባችኋል ። እርሱ
ንም ፡ ምሰሉት ፡ የምትራሩ ፡ ሰላምንም ፡ የምት
ፈልጉ ፡ ትሆኑ ፡ ዘንድ ። ንፉጎች ፡ ትሰቢተኞች ፡
ፊት ፡ አይታችሁ ፡ የምታዳሉ ፡ ኩራተኞች ፡
ያለልክ ፡ የምትበሉና ፡ የምትጠጡ ፡ አትሁኑ ።
የእግዚአብሔርን ፡ ስጦታ ፡ አታቃሉ ፡ ተቀበ
ሉት ፡ እንጂ ። እናንተ ፡ አሁን ፡ ለእግዚአብ
ሔር ፡ ደጎች ፡ መጋቢዎች ፡ ሆናችኋልና ፡
የሰጣችሁንም ፡ ሥርዓቱንና ፡ አስተዳደሩን ፡
ለእርሱ ፡ ትመልሳላችሁና ።

፻፳፯ ኤጲስቆጶስ ፡ ከምግብና ፡ ከልብስ ፡ የሚበቃ
ውን ፡ ያህል ፡ የሚወስድ ፡ ይሁን ፡ ለሚያገለ
ግል ፡ ዋጋው ፡ ይገባዋልና ። ልብሱን ፡ አያሳ
ምር ፡ ሥጋውን ፡ ለመሸፈን ፡ የሚበቃውን ፡
ያህል ፡ ይውሰድ ፡ እንጂ ። ሌላ ፡ ጌጥ ፡ የሚያስ
ፈልግ ፡ አይደለም ።

፻፳፰ በሕዝባችሁ ፡ ዘንድ ፡ እናንተ ፡ ዛሬ ፡ ካህናት ፡
ናችሁ ። እናንተ ፡ የቅድስት ፡ ደብተራ ፡ አገል
ጋዮች ፡ የሆኑ ፡ ሌዋውያን ፡ ናችሁ ፡ ይህች
ውም ፡ ጉባኤ ፡ ቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
ናት ። ከሥልጣናችሁ ፡ በታች ፡ ላሉት ፡ ሕዝብ፡
እናንተ ፡ አባቶች ፡ ናችሁ ። የሹማምት ፡ አለ
ቆች ፡ እናንተ ፡ ናችሁ ። በእግዚአብሔር ፡
ና ፡ በሰው ፡ መካከል ፡ የምታስታርቁ ፡ እናንተ፡
ናችሁ ። ኃጢአትን ፡ ሁሉ ፡ የምታስተሠርዩ ፡
ስለነርሱም ፡ መልስ ፡ የምትሰጡ ፡ እናንተ ፡
ናችሁ ። ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ከፍተኛ ፡
ዋጋ ፡ ምስጋናው ፡ ተነግሮ ፡ የማያልቅ ፡ ክብር፡
አለ ። በቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መል
ካም ፡ አገልግሎትን ፡ የምታገለግሉ ፡ እናንተ ፡
ናችሁ ። እናንተ ፡ የያንዳንዱን ፡ ኃጢአት ፡ እን
ደተሸከማችሁ ፡ እንዲሁም ፡ ከያንዳንዱ ፡ ምግ
ባችሁንና ፡ ልብሳችሁን ፡ የሚያስፈልጋችሁ
ንም ፡ ሁሉ ፡ ትቀበላላችሁ ።

፻፳፱ ድስቅ ፡ ፴ ። እንደ ፡ ብር ፡ አንጣሪዎች ፡ ብል
ሆች ፡ ሁኑ ። ኤጲስቆጶስ ፡ ወደርሱ ፡ ለሚቀር
ባቸው ፡ ሰዎች ፡ እንዲሁ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ይገ
ባል ። ተንኰልና ፡ በደል ፡ ያለባቸውን ፡ ሰዎች፡
ይፈውሳቸው ። ደዌያቸው ፡ ፈውስ ፡ የሌለው ፡
ቢሆን ፡ ግን ፡ ከእርሱ ፡ ያርቃቸው ። ሆኖም ፡
በማውገዝ ፡ ፍጹም ፡ ማራቅን ፡ ከእርሱ ፡ አያር
ቃቸው ። በሥራው ፡ ላይ ፡ ማንንም ፡ ማን ፡

እላ ፡ ለሊሁ ፡ በንፍሱ ፡ በዘይደሉ ፡ ወኢይእመን
ኵሎ ፡ ስምዐ ፡ ሐሰት ፡ በላዕሌሆሙ ።

፻፵ ወኩን ፡ ከመ ፡ ብእሴ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእ
ንኖ ፡ መንፈስከ ፤ ወኢታፅምዕ ፡ ከመ ፡ ትትወ
ከፍ ፡ ቃሎ ፡ ለመስተዋድየ፡ እኅዊሁ ፡ በሐ
ሰት ፡ በእንተ ፡ ቅንእቱ ፡ ወእከዩ ። እስመ ፡
ዘከመ ፡ እሉ ፡ ኢየኀድጉ ፡ ከመ ፡ ትኩን ፡ ሰላም ፡
ዘልፈ ፡ እበተሐይጾሙ ፡ ወተዐቀብ ፡ እምኔሆሙ
ከመ ፡ ኢታሕጕል ፡ ዘኢኮኑ ፡ ኃጥእነ ። ወለእመ
ረከብከ ፡ ጥዩቀ ፡ በከመ ፡ ውዱቶሙ ፡ ለእሉ ፡
ግቡር ፡ ውስቴቱ ፡ በከመ ፡ ትምህርቱ ፡ ለእግዚ
አብሔር ፡ ንሥእ ፡ ለዘአበተዋደይዎ ፡ ባሕቲቶ ፡
በባሕቲትከ ፡ ወገሥፆ ፡ ወሶበ ፡ ኢፈቀደ ፡ ከመ፡
ይነስሕ ፡ ስባሕቲትከ ፡ ንሣእ ፡ ምስሌከ ፡
አሐደ ፡ ሰምዐ ፡ አው ፡ ክልኤተ ፡ ወአጠይቆ ፡
በፍሥሐ ፡ ትምህርተ ፡ መንፈሳዊተ ፡ ወለእመ ፡
ሠምረ ፡ በዝንቱ ፡ ነገርከሙ ፡ ሠናየ ፡ ይከውን ፡
ሎቱ ፡ ወእመሰ ፡ ኢተመይጠ ፡ እምኔጋዩ ፡
ንግሩ ፡ ለጉባኤ ፡ ከመ ፡ ይገሥጽዎ ። ወለእመ ፡
ኢተእዘዘ ፡ ለጉባኤ ፡ ንግሩ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲ
ያን ። ወለእመ ፡ ኢሰምዓ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲ
ያን ፡ ይኩን ፡ በኀቤከ ፡ እምሳለ ፡ መጥዓዊ ፡
ወመጸብሐዊ ፡ ወኢይሳተፍከ ፡ እስከ ፡ ይኔስሕ ።
ወለእመ ፡ ነስሐ ፡ ወገብረ ፡ በከመ ፡ ገብረ ፡
መጸብሐዊ ፡ ወተመይጠ ፡ እምነ ፡ ስሕተቱ ፡
ያብእዎ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከመ ፡ ይስ
ማዕ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እስከ ፡ ይትከሠት ፡
እምኀቤሁ ፡ ፍሬ ፡ ንስሓ ።

፻፵፩ ኦ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ኢትላተፎሙ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡
ጸሎታት ፤ ዳእሙ ፡ ያውፅእዎሙ ፡ እምድኅረ ፡
አንብቦተ ፡ ወንጌል ፡ ከመ ፡ ይተከዙ ፡ ላዕለ ፡
ዘኀለፈ ፡ እምኔሆሙ ፡ ወእለ ፡ ተርፉ ፡ እምኔ
ሆሙ ፡ ይኩኑ ፡ ፍጹማነ ፡ ለጽዋዔ ፡ ወዘሂ ፡
ይሬእዮሙ ፡ ይኀዝን ፡ በእንቲአሆሙ ፡ ወይትዐ
ቀብ ፡ ከመ ፡ ኢይደቅ ውስተ ፡ ዕልወት ፡ ወይ
ፍራህ ፡ ከመ ፡ ኢይርከቦ ፡ ዘረከበ ፡ ኪያሆሙ ።
፻፵፪ ወለእመ ፡ እበስ ፡ ኃጥእ ፡ እሐደ ፡ ጊዜ ፡ አው ፡
ክልኤተ ፡ ኢትመንኖ ፡ ወኢትክልኦ ፡ እምተሳ
ትፎ ፤ ዓዲ ፡ ተሳተፍ ፡ ምስሌሆሙ ፡ በጊዜ ፡
መብልዕ ፡ ወንስሐሆሙ ፡ ተወከፍ ፡ ሎሙ ፤
ወአልብሶሙ ፡ ልብስ ፡ በአምሳለ ፡ ወልድ ፡



እይመን ፡ በሚገባ ፡ ነገር ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ ይሥ
ራው ፡ እንጂ ። በላያቸውም ፡ የሐሰት ፡ ምስክ
ርን ፡ አይመን ።

፻፵ ልብህን ፡ በማስፋት ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡
ሰው ፡ ሁን ። ስለ ፡ ቅንዓቱና ፡ ስለክፋቱ ፡ ወንድ
ሞቹን ፡ በሐሰት ፡ የሚከስውን ፡ የነገረ ፡ ሠሪ ፡
ቃል ፡ ትቀበል ፡ ዘንድ ፡ አትስማ ። እንደነዚህ ፡
ያሉት ፡ ሰዎች ፡ ሰላም ፡ ትኖር ፡ ዘንድ ፡ አይተ
ውምና ። ዘወትር ፡ ተመልከታቸው ፤ ከነር
ሱም ፡ ተጠበቅ ፡ ኃጢአተኞች ፡ ያልሆኑትን ፡
እንዳታጠፋ ። በተረዳ ፡ ሁናቴ ፡ እንደ ፡ ነገር ፡
ሥራቸው ፡ ሆኖ ፡ ብታገኘው ፡ እንደ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ትምህርት ፡ አድርግ ። (ማቴ ፡ ፲፰ ፡
፲፭ - ፲፯) ። የከሰሱትን ፡ ሰው ፡ ብቻውን ፡ አድ
ርገህ ፡ ለብቻህ ፡ ምከረው ። ብቻህን ፡ ነግረኸው
ሊመለስ ፡ ባይወድ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡
ወይም ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ይዘህ ፡ በደስታ ፡ መን
ፈሳዊ ፡ ትምህርትን ፡ አበረዳው ። ይህንንም ፡
መንፈሳዊ ፡ ትምህርታችሁን ፡ ቢቀበላችሁ ፡
በጎ ፡ ነገር ፡ ይሆንለታል ። ከስሕተቱ ፡ ባይመ
ለስ ፡ ግን ፡ ለምእመናን ፡ ንገሩ ። ቤተ ፡ ክርስቲ
ያንን ፡ ባይሰማት ፡ ግን ፡ በአንተ ፡ ዘንድ ፡ እንደ
መጥዓዊና ፡ (አረማዊ) ፡ እንደ ፡ መጸብሐዊ ፡
ይሁን ። ንስሐ ፡ እስኪገባ ፡ ድረስ ፡ ከአንተ ፡
ጋር ፡ አንድ ፡ አይሁን ። ቢመለስና ፡ መጸብ
ሐዊ ፡ እንዳደረገው ፡ ቢያደርግ ፡ ከስሕተቱም ፡
ቢመለስ ፡ የንስሐ ፡ ፍሬ ፡ ከእርሱ ፡ ዘንድ ፡ እስ
ኪገለጥ ፡ ድረስ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡
ይሰማ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያግ
ቡት ።
፻፵፩ ኤጲስቆጶስ ፡ ሆይ ፡ በጸሎት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ አት
ገናኛቸው ። ወንጌል ፡ ከተነበበ ፡ በኋላ ፡ ያስ
ወጧቸው ፡ እንጂ ። ባለፈው ፡ ዘመናቸው ፡ ይተ
ክዙ ፡ ዘንድ ፡ ከነርሱ ፡ የቀሩትም ፡ ለተጠሩበት፡
ዓላማ ፡ ፍጹማን ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ የሚያያቸ
ውም ፡ ስለነርሱ ፡ ያዝን ፡ ዘንድ ፡ በስሕተ
ትም ፡ እንዳይወድቅ ፡ ይጠበቅ ፡ ዘንድ ፡ እነር
ሱንም ፡ ያገኘ ፡ እንዳያገኘው ፡ ይፈራ ፡ ዘንድ ።
፻፵፪ ኃጥእ ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ፪ ፡ ጊዜ ፡ ቢበድል ፡
ንቀህ ፡ ከአንድነት ፡ አትለየው ፡ በምግብ ፡
ጊዜ ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ተባበር ፡ እንጂ ። ንስሐቸ
ውንም ፡ ተቀበል ፡ ተጸጽቶ ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ በተ
መለሰው ፡ ልጅ ፡ አምሳል ፡ (ሉቃ ፡ ፲፭ ፡ ፲፯ -

ዘንስሐ ፡ ወተመይጠ ፡ ኀበ ፡ አቡሁ ። ወእን
ብር ፡ እደ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ህየንተ ፡ ጥምቀት ፡
እስመ ፡ በአንብሮ ፡ እዴነ ፡ እለ ፡ ይኔስሑ ፡
ይነሥኡ ፡ ጸጋ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወሚጠሙ ፡
ኀበ ፡ ሙከኖሙ ፡ ዘቀዳሚ ።

፻፴፫ ወከመዝ ፡ ፈውሶሙ ፡ ለኃጥአን ፡ ወግበር ፡
ሎሙ ፡ መድኃኒተ ፡ ሠናየ ፡ ወልምሉመ ፡ ወአ
ጽንዖሙ ፡ በነገረ ፡ ተግሣጽ ፡ ወአፅምም ፡ ቍሰ
ላቲሆሙ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ቍሰል ፡ ሰሙቶ ፡
ወምሉእ ፡ መግል ፡ ይፈውስዎ ፡ በመድኃኒት ፡
ጽኑዕ ፡ ዘውእቱ ፡ ነገረ ፡ ተግሣጽ ፡ ወአምድኅ
ሬሁ ፡ በነገረ ፡ ኑዛዜ ። ወለእመ ፡ ሰፍሐ ፡
ቍሰል ፡ ወመተረ ፡ አባለ ፡ ወኢተረክበ ፡ ዘይ
ፌውሶ ፡ የኀሥሡ ፡ ሎቱ ፡ በጽኑዕ ፡ ሐተታ ፡
ወተዐቅቦ ፡ ወምክር ፡ ዐቃቤ ፡ ሥራይ ፡ ማእ
ምረ ፡ ወምትሮ ፡ በሕማም ፡ ወኀዘን ፡ ለአባል ፡
ዘማሰነ ፡ ከመ ፡ ኢይማስኑ ፡ መለያልያት ፡ እለ ፡
ተርፉ ። እስመ ፡ ናሁ ፡ ይቤ ፡ ጽሑፍ ፡ ምልሑ ፡
እከየ ፡ እማእከሌክሙ ፡ ወኢትኩን ፡ ዘታፈ
ጥን ፡ ለመቲር ፡ ወኢደፋሬ ፡ ወኢረዋጼ ፡ ለወ
ሚር ፡ በሞሠርት ፡ ነዊኅ ፡ አሰናን ።

፻፴፬ ወእሙኒ ፡ ኮነ ፡ መስተዋድይ ፡ ሐሳዌ ፡ ኢትሰ
ምዕዎ ። እስመ ፡ አንትሙ ፡ ለእመ ፡ ፈታሕ
ክሙ ፡ ፍትሐ ፡ ላዕለ ፩ኒ ፡ በዓመፃ ፡ አእምሩ ፡
ከመ ፡ ፍትሐ ፡ በቀል ፡ ትወፅእ ፡ እምነ ፡ አፉ
ክሙ ፡ ላዕለ ፡ ርእስክሙ ። ወለእመሰ ፡ ፈታሕ
ክሙ ፡ በኢያድልዎ ፡ አንትሙ ፡ ተእምሩ ፡
እምነ ፡ ዘያስተዋዲ ፡ ቢጾ ፡ በሐሰት ፡ ወዘንተ ፡
ሶበ ፡ አእመርከ ፡ ሐሳዌሁ ፡ በርእሱ ፡ ኰንኖ ፡
ከሡተ ፡ ወግበር ፡ ቦቱ ፡ በከመ ፡ ፈቀደ ፡ ይግ
በር ፡ ሰቢጹ ፡ ወረሰዮ ፡ ከሡተ ፡ ማእከለ ፡
ጉባኤ ፡ ከመ ፡ ቀታሌ ፡ እጉሁ ፡ ውእቱ ፡ ወሶበ ፡
ነሰሐ ፡ ሥራዕ ፡ ሎቱ ፡ ጾመ ፡ ወእምዝ ፡ አን
ብር ፡ እዴከ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወተወከፎ ፡ እምድኅረ ፡
ተአዘዘ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ኢይትመየጥ ፡ ወኢይ
ጽናዕ ፡ ኀበ ፡ ጌጋዩ ፡ ምዕረ ፡ ወካዕበ ፡ ወለእመ ፡
ኢተመይጠ ፡ እምነ ፡ እከዩ ፡ ይሰድድዎ ፡ እስመ
ገባሬ ፡ እኪት ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ኢያርኵስ ፡ ቤተ፡
ክርስቲያኑ ፡ ለእግዚአብሔር ።

፻፴፭ ወኢትፍትሑ ፡ በፍትሕ ፡ አሐዱ ፡ ላዕለ ፡
ኵሎን ፡ ኃጣውአ ፡ አኮ ፡ ፍትሑ ፡ ለዘይኤብስ ፡
በገቢር ፡ ከመ ፡ ዘይኤብስ ፡ በቃሉ ፡ አው ፡ በሕ
ሊናሁ ፡ እምሰብእሰ ፡ ቦ ፡ ዘይደሉ ፡ ላዕሌሆሙ ፡



፳፬) ። ልብሰ ፡ አልብሳቸው ፡ በጥምቀት ፡ ፈን
ታ ፡ እጅ ፡ በማኖር ፡ ባርካቸው ። ንስሐ ፡ የሚ
ገቡ ፡ ሰዎች ፡ በእጃችን ፡ በመባረክ ፡ የመን
ፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ጸጋ ፡ ያገኛሉና ። ወደቀደመ ፡
ቦታቸውም ፡ መልሳቸው ።

፻፴፫ ኃጥአንን ፡ እንዲህ ፡ እያደረግህ ፡ አድናቸው ።
በጎ ፡ ልዝብ ፡ መድኃኒትን ፡ አድርግላቸው ፡
በምክር ፡ ቃልም ፡ አድናቸው ፡ ቍስላቸውንም ፡
አድርቅላቸው ። ቍስሉ ፡ ቢጐደጉድ ፡ መግ
ልንም ፡ የተመላ ፡ ቢሆን ፡ በጽኑዕ ፡ መድኃኒት፡
ያድኑታል ፡ ይኸውም ፡ የምክር ፡ ቃል ፡ ነው ።
ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በማረጋጋት ፡ ቍስሉ ፡ ቢሰፋ ፡
ሕዋሳትንም ፡ ቢቆርጥ ፡ የሚያድነውም ፡ ቢ
ታጣ ፡ አውጥተው ፡ አውርደው ፡ በመጠበቅና፡
መክረው ፡ አዋቂ ፡ ሐኪም ፡ ይሾሉታል ። የቀ
ሩት ፡ ሕዋሳት ፡ እንዳይጐዱ ፡ የተጐዳውን ፡
አባል ፡ እያዘነህ ፡ ቍረጠው ። እነሆ ፡ መጽ
ሐፍ ፡ ክፋውን ፡ ከመካከላችሁ ፡ ለዩ ፡ ብሏልና ።
(፩ ፡ ቆሮ ፡ ፳ ፡ ፱ )። ለመቍረጥ ፡ ፈጣን ፡ አት
ሁን ፡ ደፋርም ፡ አትሁን ፡ ጥርሱ ፡ ረጅም ፡ በሆ
ነ ፡ መጋዝ ፡ ለመቍረጥ ፡ የምትሮጥ ፡ አትሁን።

፻፴፬ ነገረ ፡ ሠሪው ፡ ሐሰተኛ ፡ ቢሆን ፡ አትስሙት ።
እናንተስ ፡ በእንዱስ ፡ እንኳ ፡ በግፍ ፡ አትፍ
ረዱ ፡ የበቀል ፡ ፍርድ ፡ በራሳችሁ ፡ ላይ ፡ ከአፋ
ችሁ ፡ እንደምትወጣ ፡ እወቁ ። ባለማድላት ፡
ከፈረዳችሁ ፡ በሐሰት ፡ የሚያጣላውን ፡ ታው
ቁታላችሁ ። ሐሰተኛነቱን ፡ በራሱ ፡ ካወቅህ ፡
ገልጠህ ፡ ፍረድበት ፡ በባልንጀራው ፡ ላይ ፡
ሊያደርግ ፡ የነበረውን ፡ በእርሱ ፡ አድርግበት ።
ወንድሙን ፡ ገዳይ ፡ እንደመሆኑ ፡ በጉባኤ ፡ የተ
ገለጠ ፡ አድርገው ። ንስሐ ፡ ቢገባ ፡ ጾም ፡ ሥራ
ለት ። ንስሐ ፡ ከገባ ፡ በኋላ ፡ በእጅህ ፡ ባርከህ ፡
ተቀበለው ። ወደ ፡ ስሕተቱ ፡ ተመልሶ ፡ እንዳ
ይገባ ፡ እንድ ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ተቀበለው ።
ከኃጢአቱ ፡ ባይመለስ ፡ ግን ፡ ክፉ ፡ አድራጊ ፡
ነውና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
እንዳያረክስ ፡ ይለዩት ።

፻፴፭ በኃጢአቶች ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ፩ ፡ ፍርድ ፡ አትፍ
ረዱ ። በሥራ ፡ የሚበድል ፡ ሰው ፡ ፍርድ ፡ ”
በቃሉ ፡ ወይም ፡ በሐሳቡ ፡ እንደሚበድል ፡
ሰው ፡ ፍርድ ፡ አይደለም ። ከሰዎች ፡ ወገን ፡

ተምዕዎ ፡ ባሕቲቱ ፡ ወቦ ፡ ዘይመርዎ ፡ ላዕሌ
ሆሙ ፡ ምጽዋተ ፡ ከመ ፡ የሀቡ ፡ ለነዳያን ።
ወቦ ፡ ዘይመርዎ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ጾመ ፡ ወለካልእ
ንሂ ፡ ይሰድድዎሙ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
በአምጣነ ፡ ኃጢአቶሙ ፡ እንተ ፡ ገብርዋ ።
እስመ ፡ ሕግ ፡ ኢይኤዝዝ ፡ አሐደ ፡ ኮነኔ ፡
ላዕለ ፡ ኵሎሙ ፡ ኃጥአን ።

፻፴፯ እስመ ፡ እኮ ፡ ኮነኔሁ ፡ ከመ ፡ ኮነኔሁ ፡ ለዘ
አበሰ ፡ ላዕለ ፡ እግዚአብሔር ፡ አው ፡ ላዕለ ፡
ካህን ፡ አው ፡ ላዕለ ፡ መቅደስ ፡ ከመ ፡ ዘአበሰ ፡
በዓመፃ ፡ ላዕለ ፡ ንጉሥ ፡ አው ፡ ላዕለ ፡ አሐዱ ፡
እምነ ፡ አብያጺሁ ፡ ወኢኮነት ፡ ኮነኔሁ ፡ ከመ ፡
ዘይትኤሰይ ፡ ቤጸ ፡ ወአማብርቲሁ ፡ ወኮነኔ ፡
እምነ ፡ ዘይኤብስ ፡ ኀበ ፡ ወላድያኒሁ ፡ አው ፡
ኀበ ፡ እዝማዲሁ ። ወኢዘይኤብስ ፡ በፈቃዱ ፡
ከመ ፡ ዘይኤብስ ፡ ዘእንበለ ፡ ፈቃዱ ። እስመ ፡
ለሰብእ ፡ ይደልዎሙ ፡ ኮነኔ ፡ ቦ ፡ በቀትል ፡
ወካልአንሂ ፡ በቅሥፈት ፡ ቦ ፡ በፈድዮ ፡ ንዋ
የሙ ፡ ወለካልአንሂ ፡ ከመ ፡ ይትገበር ፡ በሙ ፡
በከመ ፡ ገብሩ ፡ ላዕለ ፡ ቢጸሙ ። እእምሩ ፡
ኮነኔ ፡ ኮሉ ፡ ኃጥአን ፡ ዘዘዚአሁ ፡ ከመ ፡ ኢይ
ኩን ፡ በኀቢክሙ ፡ ማኅሰ ። እስመ ፡ በከመ ፡
ኰነንክሙ ፡ ወፈታሕክሙ ፡ ይፈትሑ ፡ ላዕ
ሌክሙ ።

፻፴፰ ዘ፲ወ፪ቱ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ይደ
ልዎ ፡ ከመ ፡ ይስእል ፡ በዘይከውን ፡ ሰላም ፡
ላዕለ ፡ ካልአን ፡ ወይደሉ ፡ ሎቱ ፡ ፈድፋደ ፡
ከመ ፡ ይኩን ፡ ዝንቱ ፡ በኀቤሁ ፡ ወእመ ፡ አኮ ፡
እፎ ፡ ይሰነአወ ፡ ብዙኃን ፡ ለእመ ፡ ኢኮነ ፡
ዝንቱ ፡ ስኢል ፡ በኀቤሁ ። ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡
ፈቃዱ ፡ ለክርስቶስ ፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ ብዙኃን ፡
እሉ ፡ ይድኅኑ ፡ ወከመ ፡ ኢትፃእ ፡ እምነ ፡
ጉልቍ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናዊት ፡ አሐቲ ፡
ነፍስ ። ወናሁ ፡ ጽሑፍ ፡ ዘይቤ ፡ "ዘሰ ፡ ኢያ
ትጋባእ ፡ ምስሌየ ፡ ውእቱ ፡ ይዘሩ ፡ ዘሀለወ ፡
ኀቤየ" ።

፻፴፱ ወለእመ ፡ ኮንከ ፡ ፍሉጠ ፡ እምነ አባግዕ ፡
ጸላኢሆሙ ፡ አንተ ፡ ወሰይጠ ፡ ለእግዚአብ
ሔር ፡ ወማኅጕሊ ፡ አባግዕ ፡ ዘከዋሆሙ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ኖላዊ ። እፎ ፡ አንተ ፡ ትዘሩ ፡
ዘአስተጋባእናሆሙ ፡ ንሕነ እምነ ፡ አሕዛብ ፡



ቅጣ ፡ ብቻ ፡ የሚገባቸው ፡ አሉ ። ለድሆች ፡
ገንዘብ ፡ ይሰጡ ፡ ዘንድ ፡ የሚታዘዙም ፡ አሉ ።
ጾም ፡ እንዲጾሙ ፡ የሚታዘዙም ፡ አሉ ፡ ሌሎ
ቹን ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ሠሩዋት ፡ ኃጢአት ፡ መጠን፡
ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይሰዳቸዋል ።

፻፴፯ ሕግ ፡ በኃጥአን ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ፍርድን ፡
አያዝምና ፡ እግዚአብሔርን ፡ ወይም ፡ ካህ
ኑን ፡ ወይም ፡ ቤተ ፡ መቅደሱን ፡ የበደለው ፡
ሰው ፡ ፍርድ ፡ በንጉሥ ፡ ላይ ፡ ዓምፆ ፡ እንደ ፡
በደለ ፡ ሰው ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ ከጓደኞቹ ፡ አን
ዱን ፡ እንደ ፡ በደለ ፡ ሰው ፡ ፍርድ ፡ አይደለምና።
ፍርዱ ፡ ጓደኞውንና ፡ ባሮቹን ፡ እንደሚበድል ፡
ሰው ፡ ፍርድ ፡ አይደለም ። ወላጆቹን ፡ ወይም ፡
ዘመዶቹን ፡ የሚበድል ፡ ሰው ፡ ቅጣቱ ፡ አንድ፡
አይደለም ። በፈቃዱ ፡ የሚበድልና ፡ ያለፈቃዱ፡
የሚበድል ፡ ቅጣቱ ፡ አንድ ፡ አይደለም ፡ ለበ
ደሉት ፡ ሰዎች ፡ ቅጣት ፡ ይገባቸዋልና ። ሞት ፡
የሚፈረድበት ፡ አለ ፡ ሌሎችም ፡ ግርፋት ፡ የሚ
ፈረድባቸው ፡ አሉ ፡ ገንዘብ ፡ እንዲከፍሉ ፡ የሚ
ፈረድባቸው ፡ ሌሎችም ፡ በባልንጀራቸው ፡
ላይ ፡ እንዳደረጉት ፡ ያለ ፡ የሚፈረድባቸው ፡
አሉ ። በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ግፍ ፡ እንዳይፈጸም ፡
ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆነውን ፡ የኃጥአንን ፡ ፍርድ ፡
እወቁ ፡ እንደፈረዳችሁ ፡ ይፈርዱባችኋልና ።

፻፴፰ ድስቅ ፡ ፲፪ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ከሆነ ፡ በሌሎች ፡
ዘንድ ፡ ሰላም ፡ በሚጸና ፡ ገንዘብ ፡ መጸለይ ፡
ይገባዋል ። ይህ ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ሊሆን ፡ ይገ
ባል ። ይህ ፡ ካልሆነ ፡ ጸሎቱም ፡ በእርሱ ፡
ዘንድ ፡ ካልተፈጸመ ፡ ብዙዎች ፡ እንዴት ፡ ይስ
ማማሉ ። የክርስቶስ ፡ ፈቃዱ ፡ የሚድኑት ፡ የበ
ዙ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ከቤተ ፡ ክርስቲያ
ንም ፡ ቍጥር ፡ አንዲት ፡ ነፍስ እንኳ ፡ እንዳት
ጐድል ፡ ነው ። ከእኔ ፡ ጋር ፡ ያልሆነ ፡ ከእኔ ፡
ጋር ፡ ያሉትን ፡ ይበትናቸዋል ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ፡
እነሆ ፡ አለ ። (ማቴ ፡ ፲፪ ፡ ፴ ፡ ሉቃ ፡ ፲፩ ፡ ፳፫) ።

፻፴፱ ከበጎች ፡ የተለየህ ፡ ብትሆን ፡ ጠላታቸው ፡
አንተ ፡ ነህ ። የእግዚአብሔርም ፡ ባላጋራው ፡
ነህ ። እግዚአብሔር ፡ ጠባቂ ፡ የሆናቸውን ፡
በጎች ፡ የምታጠፋ ፡ አንተ ፡ ነህ ። እኛ ፡ ብዙ ፡
ቋንቋዎችን ፡ በመናገር ፡ በድካም ፡ በትጋትና ፡

ብዙኃን ፡ በልሳናት ፡ ብዙኅ ፡ በድካም ፡ ወበ ጾማ ፡ በትጋሀ ፡ ወበጾም ፡ በስኪብ ፡ ላዕለ ፡ ምድር ፡ ወተሰዶ ፡ በሙቃሔ ፡ ወሕማም ፡ ዘለ ዓለም ፡ እስከ ፡ ገበርነ ፡ ፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወእስከ ፡ መላእነ ፡ ቤቶ ፡ እምነ ፡ ሕዝብ ፡ ጽጡ ዓን ፡ ዘውእቶሙ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጉባኤ ፡ ቅድስት ።

፻፴፱ ዘ፲ወ፱ቱ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ስፋሕ ፡ እደ.ከ ፡ ዘየ ማን ፡ ወጸሐቅ ፡ ከመ ፡ መጋቢ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለፈጽሞ ፡ መፍቅዶን ፡ ለመበለታት ፡ ወለድክ ተማን ፡ ወለእለ እልሆሙ ፡ ማኅደር ፡ ወለጽ ሁቃን ፡ ወለነኮሎሙ ፡ ነዳያን ፡ ምእመናን ፡ በዘ ይሴስዩ ፡ ውሉዶሙ ፡ ወበእንተ ፡ ሕማም ፡ ዘይ ረክበሙ ።

፻፵ ዘ፲ወ፰ቱ ፡ ጸሙሁ ፡ ይከታመ ፡ በዘይተልጠ ክሙ ፡ ወጸሀቀ ለአብልዖቶሙ ፡ ወኢትኅድግ ዎሙ ፡ ይፀነሱ ፡ በምንትኒ ። ወለወሬዛዊት ፡ ድንግል ፡ ረዐዶዋ ፡ እስከ ፡ ትበጽሕ ፡ ኀበ ፡ እምጣነ ፡ ተዋስቦ ፡ ወአስተዋስብዋ ፡ ለእሐዱ ፡ እምነ ፡ ምእመናን ፡ ወከማሁ ፡ ለወሬዛኒ ፡ ካዕበ ፡ መሀርዎ ፡ ግብረ ፡ እደ ፡ ወአለብውዎ ፡ ወሴስይዎ ፡ በዘየሐዩ ፡ እስከ ፡ እመ ፡ ይክል ፡ ለቀውመ ፡ ነፍሱ ፡ በግብረ ፡ እደዊሁ ።

፻፵፩ ዘ፳ወ፩ቱ ፡ ወይደዩ ፡ ከመ ፡ ይጽሐቅ ፡ ለተ ግማጸ ፡ ሕዝባውያን ፡ ከመ ፡ ኢይገዝኩ ፡ መርገመ ፡ በአፉሆሙ ። ወከመ ፡ ይጽሐቁ ፡ በኵሉ ፡ ለለአሐዱ ፡ እመሂ ፡ ለካህን ፡ እው ፡ ለሕዝባዊ ።

፻፵፪ በስ ፡ ዘ፴ወ፱ቱ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘይለብስ ፡ ሜላተ ፡ እው ፡ ቀጠንተ ፡ እው ዘያሠረጉ ፡ ማእዶ ፡ በጣዕመ ፡ መባልዕት ፡ በዘዚእሁ ፡ እንዘ ነዳያን ፡ ሀገሩ ፡ ርኁባን ፡ እሙ ፡ ስሩቃን ፡ ኢኮነ ፡ ውእቱ ፡ ኤጲስቆጶስ ።

፻፵፫ ሣልስ ፡ ወይደልዎሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ከመ ፡ ይትእ ዘዙ ፡ ሎቱ ፡ ወይግበሩ ፡ ምስሌሁ ፡ ዘእዘዞሙ ።

፻፵፬ ድስቅ ፡ ዘ፰ቱ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ውእቱ ፡ እኩክሙ፡ እምታሕተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘወለደክሙ ፡ ዳግመ ፡ እማይ ፡ ወእመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ እምላክክሙ ፡ በዲበ ፡ ምድር ፡ እምታ



በጾም ፡ ከመሬት ፡ ላይ ፡ በመተኛትና ፡ በመስ ደድ ፡ በመታሰርና ፡ ዘወትር ፡ በመታመም ፡ የእ ግዚአብሔርን ፡ ፈቃድ ፡ እስከመፈጸም ፡ ደርሰ ንና ፡ ከተጠሩት ፡ ሰዎች ፡ ወገን ፡ ቤቱን ፡ እስከ፡ መምላት ፡ ደርሰን ፡ ከብዙ ፡ ነገድ ፡ ውስጥ ፡ የሰ በሰብናቸውን ፡ ምእመናን ፡ አንተ ፡ እንደ.ት ፡ ትበትናለህ ፡ እነርሱም ፡ የቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክር ስቲያን ፡ ጉባኤ ፡ ናቸው ።

፻፴፱ ድስቅ ፡ ፲፱ ። ኤጲስቆጶስ ፡ ሆይ ፡ ለመስጠት ፡ ቀኝ ፡ እጅህን ፡ ዘርጋ ። እግዚአብሔር ፡ የሾ መህ ፡ መጋቢ ፡ እንደመሆንህ ፡ ረዳት ፡ የሌላ ቸውን ፡ ባልቴቶቹን ፡ ደካሞቹን ፡ ቤት ፡ የሌላ ቸውን ፡ የተጨነቁትን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ያመ ኑትን ፡ ድሆቹን ፡ ለመርዳት ፡ ልጆቻቸውን ፡ በሚመግቡ ፡ ገንዘብ ፡ የሚመግቡበትንና ፡ ስለ ሚያገኙቸውም ፡ መከራ ፡ ለመርዳት ፡ ትጋ ።

፻፵ ድስቅ ፡ ፲፰ ። ይከተሏቸው ፡ ዘንድ ፡ ድሀ ፡ አደ ጎቹን ፡ ጥሩ ፡ እነርሱን ፡ ለመመገብ ፡ ትጉ ፡ በማናቸውም ፡ ነገር ፡ ይቸገሩ ፡ ዘንድ ፡ አትተ ዋቸው ። ሕፃንነት ፡ ያላትንም ፡ ድንግል ፡ እካለ ፡ መጠን ፡ እስከታደርስ ፡ ድረስ ፡ ጠብ ቋት ፡ ከምእመናንም ፡ ለአንዱ ፡ አጋቧት ። እንደዚሁም ፡ ሕፃንነት ፡ ያለውን ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ተግባረ ፡ እደ ፡ አስተምሩት ። መጽሐ ፍን ፡ አስተምሩት ። ሥራ ፡ ሠርቶ ፡ ራሱን ፡ ችሎ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ መግቡት ።

፻፵፩ ድስቅ ፡ ፳፪ ። በአፋቸው ፡ መርገም ፡ እንዳያና ገሩ ፡ ሕዝቡን ፡ ለመገሠጽ ፡ ይተጋ ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ። ለካህን ፡ ወይም ፡ ለሕዝባዊ ፡ ቢሆን ፡ ለያንዳንዱ ፡ በሥራው ፡ ሁሉ ፡ ይተጉ ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ።

፻፵፪ በስ ፡ ፴፱ ። ሐር ፡ ወይም ፡ ቀጭን ፡ ልብስ ፡ የሚ ለብስ ፡ ወይም ፡ በአገሩ ፡ ነዳያን ፡ ተርበውና ፡ ታርዘው ፡ ሳሉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጣዕም ፡ ባለው ፡ ምግብ ፡ ማዕድን ፡ የሚያስጌጥ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አይደለም ።

፻፵፫ ሦስተኛ ፡ ሕዝቡ ፡ ለርሱ ፡ መታዘዝና ፡ ያዘዛቸ ውንም ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ መሥራት ፡ ይገባቸ ዋል ።

፻፵፬ ድስቅ ፡ ፰ ። ከውሀና ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዳግመኛ ፡ ከወለዳቸው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በታ ች ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ አባታችሁ ፡ ነው ። በእው ነት ፡ ገዥ ፡ ከሆነው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በታች ፡

ሕተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ዘበእማን ። ወእግዚአብሔር ፡ ይቤ ፡ በአፈ ፡ ዳዊት ፡ ነቢይ ፡ "እንሰ ፡ እቤ ፡ አማልክት ፡ አንትሙ ፡ ወደቂቀ ፡ ልዑል ፡ ኵልክሙ ፡ ወካዕበ" ፡ ይቤ ፡ ኢትበል ፡ እኩየ ፡ ላዕለ ፡ አማልክት ፡ ወእሉ ፡ እሙንቱ ፡ ኤጲስቆጶሳት ።

፻፵፭ ዘኒተ ፡ በእንተ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እ ፡ ብእሲ ፡ ሰመየከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሎቱ ፡ ወልደ ፡ እእምር ፡ በዝንቱ ፡ መጠነ ፡ አክበረከ ፡ ወአክብሮ ፡ ለዘኮነከ ፡ ምክንያተ ፡ ለዝንቱ ፡ መዓርግ ፡ ዐቢይ ። እኮኑ ፡ ይቤ ፡ መጽሐፍ ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ወለዱከ ፡ በሥጋ ፡ አክብር ፡ "እባከ ፡ ወእመከ ፡ ከመ ፡ ትኩን ፡ ለከ ፡ ሕይወት" ። ወዘሰ ፡ ይቤ ፡ "ቃለ ፡ ሕሡመ ፡ ላዕለ ፡ እቡሁ ፡ እው ፡ ላዕለ ፡ እሙ ፡ ሞተ ፡ ለይሙት" ። እፎኑ ፡ ኢይደልወክሙ ፡ ከመ ፡ ታክብርዎሙ ፡ ፈድፋደ ፡ ለአበዊክሙ ፡ መንፈሳውያን ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ እስተብቋዕያን ፡ ለክሙ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወወለዱክሙ ፡ ዳግመ ፡ በማይ ፡ ወበመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወሴሰዩክሙ ፡ ሐሊበ ፡ ዘውእቱ ፡ ነገረ ፡ ትምህርት ፡ ወእጽንዑክሙ ፡ በቀኖናቲሆሙ ፡ ወረሰዩክሙ ፡ ድልዋነ ፡ ለተወክፎ ፡ ሥጋ ፡ መድኀን ፡ ወደም ፡ ክቡር ፡ ዘውእቱ ፡ ደመ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወእሙንቱ ፡ እንጽሑክሙ ፡ እምኵሉ ፡ እበሳክሙ ፡ ወረሰዩክሙ ፡ ድልዋነ ፡ ለጸጋሁ ፡ ቅዱስ ፡ ወሱቱፋነ ፡ ለርስቱ ።

፻፵፮ ፍርሀዎሙ ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ተጸገዉ ፡ ሥልጣነ ፡ ሕይወት ፡ ወሞት ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብብሔር ፡ ከመ ፡ ይኰንንዎ ፡ ለዘአበሰ ፡ ወይፍትሑ ፡ ላዕሌሁ ፡ ተኰንኖ ፡ በእሳት ፡ ዘለዓለም ። ወሶበ ፡ ነሥሐ ፡ ይስረዩ ፡ ሎቱ ፡ ኃጢአቶ ፡ ወያሕይውዎ ። ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ይደልወክሙ ፡ ከመ ፡ ታፈቅርዎ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ በፍቅረ ፡ አብ ፡ ወትፈርህዎ ፡ ከመ ፡ ንጉሥ ፡ ወታከብርዎ ፡ አምሳለ ፡ እግዚአብሔር ።

፻፵፯ አንተኒ ፡ ይደልወከ ፡ ከመ ፡ ተሀበ ፡ ዘይደልዎ ፡ ወለውእቱኒ ፡ ይደሉ ፡ ላዕሌሁ ፡ ከመ ፡ ያሠኒ ፡ ምግብናሁ ፡ ዘተጸገወ ። እስመ ፡ ውእቱ ፡ መኰንን ፡ ዘኀረዮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሠሪዐ ፡ ግብር ፡



በዚህ ፡ ዓለም ፡ ገዦችሁ ፡ ነው ። እግዚአብሔርም ፡ በነቢዩ ፡ በዳዊት ፡ አፍ ፡ "እኔ ፡ ግን ፡ እናንተ ፡ አማልክት ፡ ናችሁ ፡ ሁላችሁም ፡ የልዑል ፡ ልጆች ፡ ናችሁ ፡ አልሁ ፡" ብሏል ። (መዝ ፡ ፹፩ ፡ ፮) ። ዳግመኛም ፡ በገዢዎች ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ አትናገር ፡ አለ ። (ዘፀ ፡ ፳፪ ፡ ፳፰) ። እነዚሁም ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ናቸው ።

፻፵፭ ድስቅ ፡ ፯ ። ስለ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሲናገር ፡ ሰው ፡ ሆይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጁ ፡ ነህ ፡ አለህ ፡ በዚህ ፡ እንዴት ፡ እንዳከበረህ ፡ እወቅ ፡ ለዚህ ፡ ከፍተኛ ፡ ማዕረግ ፡ ምክንያት ፡ የሆነህን ፡ አክብረው ፡ መጽሐፍ ፡ "ሕይወት ፡ ትሆንልህ ፡ ዘንድ ፡ በሥጋ ፡ የወለዱህን ፡ አባትና ፡ እናትህን ፡ አክብር ፡" (ዘፀእ ፡ ፳ ፡ ፲፪ ። ፳፩ ፡ ፲፯) ። ያለ ፡ አይደለምን ። በአባቱ ፡ ወይም ፡ በእናቱ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ቃል ፡ የተናገረ ፡ ግን ፡ ሞትን ፡ ይሙት ፡ ብሎ ፡ የለምን ፡ (ዘዳ ፡ ፳፩ ፡ ፲፰ - ፳፩) ። መንፈሳውያን ፡ አባቶቻችሁንማ ፡ እንዴት ፡ በብዙ ፡ ልታከብሩዋቸው ፡ አይገባችሁም ፡ እነሱ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ አማላጆቻችሁ ፡ ናቸውና ። ከውሀና ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ዳግመኛ ፡ ወለዷችሁ ። ወተት ፡ መገቧችሁ ፤ ይኸውም ፡ የትምህርት ፡ ነገር ፡ ነው ። በሕጋቸውም ፡ አጸኑዋችሁ ፤ የሚያድን ፡ ሥጋንና ፡ የከበረ ፡ ደምን ፡ ለመቀበል ፡ እንድትበቁ ፡ አደረጓችሁ ፡ ይኸውም ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ደም ፡ ነው ። እነርሱ ፡ ከኀጢአታችሁ ፡ ሁሉ ፡ አነጹችሁ ። የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ጸጋ ፡ ለመቀበል ፡ የበቃችሁና ፡ የርስቱ ፡ ተካፋዮች ፡ አደረጓችሁ ።

፻፵፮ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የሕይወትና ፡ የሞት ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጥቷቸዋልና ፡ አክብሩዋቸው ። የበደለውን ፡ ይቀጡ ፡ ዘንድ ፤ ዘለዓለማዊ ፡ የእሳት ፡ ቅጣትንም ፡ ይፈርዱ ፡ ዘንድ ፡ ንስሓ ፡ ቢገባ ፡ ግን ፡ ኃጢአቱን ፡ አስተሥርየው ፡ ያድኑት ፡ ዘንድ ። ስለዚህም ፡ ኤጲስቆጶሱን ፡ በአባት ፡ ፍቅር ፡ ልታፈቅሩት ፡ ይገባል ፤ እንደ ንጉሥም ፡ ልትፈሩት ፤ እንደ ፡ እግዚአብሔርም ልታከብሩት ፡ ይገባችኋል ።

፻፵፯ አንተም ፡ የሚገባውን ፡ ልትሰጠው ፡ ይገባል ። እርሱም ፡ የተቀበለውን ፡ ሹመት ፡ ሊያቃናልህ፡ ይገባዋል ። የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ እግዚአብሔር ፡ የመረጠው ፡ ሹም ፡

ቤተ ፡ ክርስቲያናዊት ፡ ወኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ትት ሐሰቦ ። ወፍጻሜሁ ፡ ለዝ ፡ ቃል ፡ ተጽሕፈ ፡ በአንቀጸ ፡ ምጽዋት ።

፻፵፰ ዘኒቅያ ፡ ዘ፵ወ፪ቱ ፡ ወይኩን ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ሀገር ፡ ሥሩዐ ፡ በረከተ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በአም ጣነ ፡ ክሂሎታ ፡ ወያምጽአዋ ፡ ኪያሃ ፡ ኀቤሁ ፡ ቀሳውስት ፡ በኵሉ ፡ ዓመታት ፡ ወኀበ ፡ ሰብአ ፡ ሀገር ፡ ወአድባር ፡ ዐዊዶሙ ፡ ያምጽኡ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይትራዳእ ፡ በውእቱ ፡ መፍቅዶ ።

፻፵፱ ድስቅ ፡ ዘ፪ቱ ፡ እመቦ ፡ ዘይተሉ ፡ ኖላዌ ፡ አኩየ ፡ ሞቱ ፡ ከሡት ፡ በቅድሜሁ ።

፻፶ ረስጣ ፡ ዘ፶ወ፬ቱ ፡ አመቦ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘፈ ቀደ ፡ በሕጸተ ፡ እእምሮቱ ፡ በቀለ ፡ ኢኮነ ፡ ውእቱ ፡ ኤጲስጳቆስ ። ዳእሙ ፡ ስም ፡ ሕሰው ፡ ሀሎ ፡ ላዕሌሁ ፡ እኮ ፡ ውእቱ ፡ እምኀበ ፡ እግዚእ ብሔር ፡ ዳእሙ ፡ እምኀበ ፡ ሰብአ ።

፻፶፩ ራብዕ ፡ በእንተ ፡ ሀልዎቱ ፡ ምስለ ፡ ካህናት ፡ ወምስለ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ወምስለ ፡ ካህና ትሰ ፡ ባሕቲቶሙ ፡ ፈድፋደ ፡ ይቤሎ ፡ ጳው ሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ለቲቶ ፡ ረድኡ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ “እእምር ፡ ከመ ፡ አነ ፡ ኀደጉከ ፡ ታሠኒ ፡ ግብረ ፡ ዘሐፀ ፡ ወትሢም ፡ ቀሲሳነ ፡ በውስተ ፡ ሀገር ፡ ወአህጉር ፡ እለ ፡ አልቦሙ ፡ ነውር ፡ ላዕሌ ሆሙ” ። ወፍጻሜ ፡ ዝንቱ ፡ ሀሎ ፡ በአንቀጸ ፡ ቀሳውስት ። ወነዋ ፡ ይነግር ፡ በአንቀጸ ፡ ቅዳሴ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ይቁም ፡ በቅድመ ፡ ምሥዋዕ ፡ ወከመ ፡ ይዝክሩ ፡ ስሞ ፡ በኵሉ ፡ ጸሎት ።

፻፶፪ ረስጣ ፡ ዘ፶ወ፫ቱ ፡ ወኢይትዐበይ ፡ ኤጲስቆ ጶስ ፡ ላዕለ ፡ ቀሳውስት ፡ ወዲያቆናት ፡ ወቀሳ ውስትኒ ፡ ላዕለ ፡ ዲበ ፡ ሕዝብ ።

፻፶፫ ዘ፳ወ፩ዱ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ይባርክ ፡ ወኢይባርክ ፡ ኪያሁ ፡ ወይሢም ፡ ሰብአ ፡ ወይትወከፍ ፡ እውሎ ግያ ፡ እምኀበ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ወአኮ ፡ እም ኀበ ፡ ቀሳውስት ፡ ወይምትር ፡ ኵሎ ፡ ካህነ ፡ ዘይደልዎ ፡ ምትረት ፡ ዘእንበለ ፡ ኤጲስቆጶስ ። እስመ ፡ ሎቱስ ፡ ኢይደልዎ ፡ ይግበር ፡ ዘንተ ፡ እምኀቤሁ ፡ በባሕቲቱ ።

፻፶፬ ዘኒቅያ ፡ ፳ወ፪ቱ ፡ ወይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይጽሐፍ ፡ ወያእምር ፡ ኵሎ ፡ መዓርጋተ ፡ ካህናት ፡ ወሥር ዓታቲሆሙ ፡ ከመ ፡ ኢይኩን ፡ ማእከሌሆሙ ፡



ነውና ። ልትቆጣጠረውም ፡ አይገባህም ። የዚህ ቃል ፡ ፍጻሜ ፡ በአንቀጸ ፡ ምጽዋት ፡ ተጽፎ አል ። (ፍትሐ ፡ ነገ ፡ ፲፮ ፡ ፭፻፵፬) ።

፻፵፰ ኒትያ ፡ ፵፪ ። የኤጲስቆጶሱ ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ በያ ገሩ ፡ እንደ ፡ ችሎታዋ ፡ መጠን ፡ ይታዘዝ ። ቀሳውስት ፡ ይህችን ፡ በየመቱ ፡ ወደርሱ ፡ ያምጧት ። በዚህ ፡ ገንዘብ ፡ ሊረዳ ፡ የሚሻውን ፡ ይረዳ ፡ ዘንድ ፡ በየከተማውና ፡ በየገጠሩ ፡ ዞረ ው ፡ ያምጡለት ።

፻፵፱ ድስቅ ፡ ፪ ። ክፉ ፡ ጠባቂን ፡ የሚከተል ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ሞቱ ፡ በፊቱ ፡ የተገለጠ ፡ ነው ።

፻፶ ረስጣ ፡ ፶፬ ። በእእምሮው ፡ ጕድለት ፡ ምክን ያት ፡ በቀልን ፡ የሚሻ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ቢኖር ፡ እርሱ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አይደለም ፤ በሐሰት ፡ ኤጲ ስቆጶስ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ ሹመቱም ፡ ከእግዚ አብሔር ፡ ዘንድ ፡ የተገኘ ፡ አይደለም ፤ ከሰው ፡ የተገኘ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፻፶፩ አራተኛው ፡ ከካህናትና ፡ ከሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ጋር ፣ ይልቁንም ፡ ከካህናት ፡ ጋር ፡ መኖር ፡ እንደሚገባው ፡ ይናገራል ። ሐዋርያው ፡ ጳው ሎስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ለሆነው ፡ ለደቀመዝሙሩ ፡ ለቲቶ ፡ “የጐደለውን ፡ ትሞላ ፡ ዘንድ ፣ ነውር ፡ የሌለባቸውንም ፡ ሰዎች ፡ በከተማና ፡ በገጠር ፡ ቀሳውስት ፡ አድርገህ ፡ ትሾም ፡ ዘንድ ፡ እንደ ተውሁህ እወቅ ፡” አለው ። (ቲቶ ፡ ፩ ፡ ፭) ። የዚህም ፡ ፍጻሜ ፡ በአንቀጸ ፡ ቀሳውስት ፡ አለ ። (ፍትሐ ፡ ነገ ፡ ፮ ፡ ፪፻፶፫) ። በመሠዊያው ፡ ፊት እንዲቆም ፣ ስሙንም ፡ በጸሎት ፡ ሁሉ ፡ እንዲ ያነሡ ፡ እነሆ ፡ በአንቀጸ ፡ ቅዳሴ ፡ ተነግሮ አል ። (ፍትሐ ፡ ነገ ፡ ፲፪ ፡ ፭፻፳፰) ።

፻፶፪ ረስጣ ፡ ፶፫ ። ኤጲስቆጶስ ፡ በቀሳውስትና ፡ በዲ ያቆናት ፡ ላይ ፡ አይታበይ ፤ ቄሶችም ፡ እንዲሁ ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ አይታበዩ ።

፻፶፫ ፳፩ ። ኤጲስቆጶስ ፡ ይባርክ ፡ እርሱን ፡ ግን ፡ አይባርኩት ። ሰዎችን ፡ ይሹም ። ከቄሶች ፡ ያይደለ ፡ ከኤጲስቆጶሳት ፡ ዘንድ ፡ አውሎጊያ ፡ (ቡራኬ) ፡ ይቀበል ። ሊሻር ፡ የሚገባውን ፡ ካህን ፡ ሁሉ ፡ ይሻር ፤ ይኸውም ፡ ከኤጲስቆጶስ ፡ በቀር ፡ ነው ፤ ኤጲስቆጶስ ፡ ብቻውን ፡ ይህን ፡ ማድረግ ፡ አይገባውምና ።

፻፶፬ ኒቅያ ፡ ፳፪ ። የካህናቱን ፡ መዓርጋትና ፡ ሥርዓ ታቸውን ፡ ጽፎ ፡ ማወቅ ፡ ይገባዋል ። በዚህ ፡ ሥራ ፡ በመካከላቸው ፡ ጠብ ፡ ክርክር ፡ እንዳይ

ኃእዝ ፡ በዝንቱ ፡ ግብር ። ወከመ ፡ ኢይደመሩ ፡ ስብአ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንተ ፡ ሐዋርያት ፡ ምስለ ፡ ሕዝባውያን ፡ በመዓርግ ፡ ወእመ ፡ እኮ ፡ ምስለ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ በእምሳሊሆሙ ።

፻፶፩ ድስቅ ፡ ዘ፳ቱ ፡ ኩኑ ፡ አ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ በበይናቲክሙ ፡ በአሐዱ ፡ ልብ ፡ ወተሳተፋዎሙ ፡ በጊዜ ፡ ሕማም ፡ ወአሕይዎሙ ፡ ለአኃው ፡ ወረዐይዎሙ ፡ ለሕዝብ ፡ በተሰናእዎ ፡ ወበንጽሐ ፡ ልብ ፡ ለመድኃኒተ ፡ ዚአሆሙ ። ወመሀርዎሙ ፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ በአሐዱ ፡ ፈቃድ ፡ ወበአሐዱ ፡ መንፈስ ፡ በሐዱ ፡ ሥጋ ። ወድልዋን ፡ በአሐዱ ፡ ኃልዮ ፡ ወበአሐዱ ፡ ምክር ፡ በከመ ፡ አዘዘ ፡ እግዚእነ ።

፻፶፪ ረስጠብ ፡ ዘ፲ቱወ፭ዱ ፡ ወኢይደልዎ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ከመ ፡ ይኅድግ ፡ መንበሮ ፡ ወሀገሮ ፡ ወይሑር ፡ ኀበ ፡ ካልእ ፡ ሀገር ፡ ዘእንበለ ፡ ከመ ፡ ይዕርቅ ፡ ካልኣኒሁ ፡ ኤጲስቆጶሳተ ፡ እለ ፡ ከማሁ ፡ ዘቦሙ በቍዔት ፡ ለሰብአ ፡ ይእቲ ፡ ብሔር ፡ በውስቴ ፡ ሕጎሙ ፡ በእንተ ፡ ሥርዓተ ፡ አበሳሆሙ ፡ ወይንበር ፡ እስከ ፡ ይትፌጸም ፡ መፍቅዶሙ ።

፻፶፫ ዘኒቅያ ፡ ዘ፯ቱ ፡ ወኢይትወከፍ ፡ እሐዱሂ ፡ እምኤጲስቆጶሳት ፡ ብእሴ ፡ ዘአውገዞ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ካልኡ ፡ ኢእምኔ ፡ ካህናት ፡ ወኢእምኔ ፡ መነኮሳት ፡ ወእምሕዝባውያንሂ ፡ ካዕበ ፡ ወኢይፍታሕ ፡ ዘአውገዞ ፡ ወኢይግበር ፡ ሎቱ ፡ ሥርዓተ ፡ ጸሎት ፡ ከመ ፡ ኢይኩን ፡ ውእቱ ፡ አስተቃልሎ ፡ ለዘአውገዞ ፡ ኤጲስቆጶስ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዝኩ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አኩየ ፡ ወገፋዔ ፡ በዘተዐውቀ ፡ በነቢይሆሙ ፡ ተዓድዎቱ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይልእኩ ፡ ኀበ ፡ ጳጳስ ፡ ዘላዕሌሁ ፡ ውኀበ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ እለ ፡ ከማሁ ፡ ከመ ፡ ይጽሐፉ ፡ ሎቱ ፡ በእንተ ፡ ግብሩ ፡ ወይንግርዎ ፡ ወእመሰ ፡ እበየ ፡ ይረድ ፡ እመዓርጊሁ ።

፻፶፬ ዘ፸ወ፯ቱ ፡ ወኢይሑር ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ኀበ ፡ ካልእ ፡ ሀገር ፡ እምነ ፡ ሀገሩ ፡ ዘኮነ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወተሠይመ ፡ ኤጲስቆጶስና ፡ በእንተ ፡ ራኅበ ፡ ብሔር ፡ ወናእስ ፡ ዚአሃ ፡ ወውኅደተ ፡ ስብእ ፡ ወበረከታቲሃ ፡ ወበእንተዝ ፡ ከመ ፡ ይኅሥሥ ፡ ለዘውእቱ ፡ ይኄይስ ፡ እምኔሃ ። እስመ ፡ ዝንቱሰ ፡ ዘኢይድልው ፡ ሎቱ ፡ አላ ፡ ለኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ተውህቦ ፡ መክፈልት ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብ



ሆን ፡ ሐዋርያት ፡ የመሠረቷት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰዎችም ፡ በመዓርግ ፡ ከሕዝባውያን ፡ ጋር ፡ እንዳይተካከሉ ፡ ይህም ፡ ባይሆን ፡ በእነርሱ ፡ እምሳል ፡ ከሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ጋር ፡ እንዳይገናኙ ።

፻፶፩ ድስቅ ፡ ፰ ። ኤጲስቆጶሳት ፡ ሆይ ፡ እርስበርሳችሁ ፡ አንድ ፡ ልብ ፡ ሁኑ ። በመከራም ፡ ጊዜ ተባበሩዋቸው ። ወንድሞችን ፡ አድኗቸው ለድኅነታቸውም ፡ በንጹሕ ፡ ልቡና ፡ በመስማማት ፡ ሕዝቡን ፡ ጠብቋቸው ። በአንድ ፈቃድ ፡ በአንድ ፡ መንፈስ ፡ በአንድ ፡ አካል ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ጌታችን ፡ እንዳዘዘ ፡ በአንድ ሐሳብ ፡ በአንድ ፡ ምክር ፡ የተዘጋጁ ፡ ይሆኑ ዘንድ ። (ዮሐ ፡ ፲፯ ፡ ፳ - ፳፫) ።

፻፶፪ ረስጠብ ፡ ፲፭ ። ኤጲስቆጶስ ፡ መንበሩንና ፡ ሀገረ ፡ ስብከቱን ፡ ይተው ፡ ወደሌላም ፡ አገር ፡ ይሄድ ፡ ዘንድ ፡ አይገባውም ። በሕጋቸው ፡ ውስጥ ፡ ኃጢአታቸውን ፡ ለማስተሥረይ ፡ ለዚያች ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ጥቅም ፡ ያላቸውን ፡ ወንድሞቹን ፡ ለማስታረቅ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሊሄድ ፡ አይገባውም ። ፈቃዳቸውም ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ይቈይ ።

፻፶፫ ኒቅያ ፡ ፯ ። ከኤጲስቆጶሳት ፡ ወገን ፡ አንዱ ፡ ሰንኳ ፡ ሌላው ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ያወገዘውን ፡ ከካህናት ፡ ወይም ፡ ከመነኮሳት ፡ ዳግመኛም ፡ ከሕዝባውያን ፡ ወገን ፡ ቢሆን ፡ አይቀበል ። ያወገዘውንም ፡ አይፍታ ፡ ጸሎተ ፡ ሥርዓትም ፡ አይድገምለት ። ያወገዘውን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ማቃለል ፡ እንዳይሆን ። ይህም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ክፉ ፡ በደለኛም ፡ ቢሆን ፡ መተላለፉ ፡ በእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ በታወቀ ፡ ገንዘብ ፡ ስለሥራው ፡ ፈጽመው ፡ ይነግሩት ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ እርሱ ፡ ወደእሉ ፡ ኤጲስቆጶሳትና ፡ ወደበላዩ ፡ ጳጳስ ፡ ሊልኩ ፡ ይገባል ፡ አንቢ ፡ ቢል ፡ ከመዓርጉ ፡ ይዋረድ ።

፻፶፬ ኒቅያ ፡ ፸፯ ። ኤጲስቆጶስ ፡ በአገሩ ፡ መስፋትና ፡ መጥበብ ፡ በሕዝቡ ፡ ማነስና ፡ ብዛት ፡ ምክንያት ፡ ኤጲስቆጶስነት ፡ ከተሾመበት ፡ አገር ፡ ወጥቶ ፡ ወደሌላ ፡ አገር ፡ አይሂድ ። ስለዚህም ፡ ከእርስዋ ፡ የሚሻለውን ፡ ሊፈልግ ፡ አይገባውም ፡ ይህ ፡ ለእርሱ ፡ አይገባውምና ። ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ድርሻው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተሰጥቶታል ፡ እንጂ ። ይህ ፡ ከሕዝባውያን ፡ ወገን ፡

ሐበ ። ወዘንተሰ ፡ ይትሜሰል ፡ አምሳለ ፡ እለ ፡ አውሰቡ ፡ ብእሲተ ፡ እምነ ፡ ሕዝባውያን ፡ ለእመ ፡ ተዐቅፈ ፡ ብእሲ ፡ በብእሲት ፡ ዘእንበለ ፡ በምክንያተ ፡ ዝሙት ፡ ለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ወልዑታ ፡ በዘትሜኒ ፡ እምኔሃ ፡ ውእቱ ፡ መአብሰ ፡ ፈድፋደ ። ወከማሁኬ ፡ ኤጲስቆጶሳትኒ ፡ ወካህናት ፡ እለ ፡ የኀሥሡ ፡ ፈድፋደ ፡ ዘይኄይስ ፡ እምሀገሮሙ ፡ በእንተዝ ፡ አውገዝናሆሙ ፡ ወመተርናሆሙ ። እስመ ፡ ዝንቱሰ ፡ ልማድ ፡ እኩይ ፡ ውእቱ ።

፻፶፱ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ምክንያት ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ በዘይሰድድዎ ፡ እምነ ፡ ሀገሩ ፡ እስከ ፡ ኢይረክብ ፡ መካነ ፡ በዘይፈልስ ፡ እምኔሃ ፡ ይእተ ፡ ጊዜ ፡ ብዉሕ ፡ ሎቱ ፡ ወይደልዎ ፡ ይሰድድዎ ፡ ካልእተ ፡ ሀገረ ፡ እምከመ ፡ አእመሩ ፡ ንጽሐ ፡ ዚአሁ ፡ ወሠናየ ፡ መግቦቱ ፡ ወሃይማኖቱ ፡ ከመ ፡ ኢተወለጠ ፡ በዝንቱ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ድልወ ፡ ያፈልስዎ ፡ ኀበ ፡ ዘይትሌዓል ፡ እስመ ፡ አኮ ፡ በፍትወተ ፡ ልቡ ፡ ዘፈለሰ ፡ እመካኑ ።

፻፷ ድስቅ ፡ ዘ፲ወ፩ዱ ፡ ወለእመ ፡ በጽሐ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ኀበ ፡ መንበረ ፡ ካልኡ ፡ እንዘ ፡ የኀሥሥ ፡ ክብረ ፡ ወውዳሴ ፡ ወነበረ ፡ ባቲ ፡ ነዋኀ ፡ ዘመነ ፡ በእንተ ፡ ዘሠነየ ፡ ፍልሰቱ ፡ ወአእመረ ፡ ሕጸተ ፡ አእምሮቱ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ በዓለ ፡ ውእቱ ፡ መንበር ፡ ዘመጽአ ፡ ኀቤሁ ፡ መፍትው ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ኢይመንኖ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ በዓለ ፡ መንበር ፡ ወኢያስተሐቅሮ ፡ ወኢያባርኮሙ ፡ ለእለ ፡ ይፈቅዱ ፡ በረከተ ፡ ፍጹመ ፡ እምነ ፡ ካህናት ፡ ዳእሙ ፡ ይኩን ፡ ቡራኬ ፡ ለበዓለ ፡ መንበር ፡ ከመ ፡ ኢይመንንዎ ፡ ሰብኡ ። ወይደሉ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ኢይሚም ፡ ወኢይትኀንዲ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያን ። ወኢይደልዎ ፡ ይድኅር ፡ ውስተ ፡ ገቢረ ፡ መፍቅዳቲሁ ፡ ዘይበዝኅ ፡ እምሠለስቱ ፡ ሰናብት ። ወእመኒ ፡ ተርፈ ፡ ውስተ ፡ መካኑ ፡ በእንተ ፡ ግብረ ፡ እደዊሁ ፡ ኢያብዝኅ ፡ ሰብአ ፡ ዘእንበለ ፡ ሠለስቱ ፡ እደው ።

፻፷፩ ረስጠ፳ ፡ ዘ፸ ፡ ኢይትወከፉ ፡ ስምዐ ፡ ሐራ ፡ ጥቃ ፡ ዘውእቶሙ ፡ በላውያን ፡ ላዕለ ፡ ኤጲስቆጶስ ።

፻፷፪ ረስጠብ ፡ ዘ፲ወ፪ቱ ፡ ወኢይትወከፉ ፡ ላዕሌሁ ፡ ስምዐ ፡ እሐዱ ፡ ኤጲስቆጶስ ።

፻፷፫ ኃምስ ፡ በእንተ ፡ ተጋብአቶሙ ፡ ለኤጲስቆጶሳት ፡ ወውእቱ ፡ በኵሉ ፡ ዓመታት ፡ ፪ተ ፡ ጊዜ ፡

ሚስት ፡ ያገቡ ፡ ሰዎችን ፡ ይመስላል ። ያለዝሙት ፡ ምክንያት ፡ ሰው ፡ ከሚስቱ ፡ ቢሰነካከል ፡ ከእርሰዋ ፡ በምትበልጥ ፡ ሊለውጣትም ፡ ቢፈልግ ፡ እርሱ ፡ በጣም ፡ በደለኛ ፡ ነው ። ከአገራቸው ፡ የተሻለ ፡ አገርን ፡ የሚፈልጉ ፡ ኤጲስቆጶሳትም ፡ ካህናትም ፡ እንደዚሁ ፡ ናቸው ። ስለዚህም ፡ አውግዘን ፡ ለየናቸው ። ይህ ፡ ልማድ ፡ መጥፎ ፡ ነውና ።

፻፶፱ ኤጲስቆጶሱ ፡ የሚሰደድበት ፡ አገር ፡ እስኪያገኝ ፡ ድረስ ፡ ደርሶ ፡ ምክንያቱ ፡ በሚያሳድዱት ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ይገባዋል ። ንጽሕናውና ፡ የአስተዳደሩ ፡ ችሎታ ፡ ሃይማኖቱም ፡ በዚህ ፡ እንዳልተለወጠ ፡ ካወቁ ፡ ወደሌላይቱ ፡ አገር ፡ ሊሰዱት ፡ ይገባዋል ። ያፈልሱት ፡ ዘንድ ፡ የሚበቃ ፡ ከሆነም ፡ ወደ ፡ ከፍተኛ ፡ መዓርግ ፡ ያውጡት ። ከቦታው ፡ የወጣ ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ አይደለምና ።

፻፷ ድስቅ ፡ ፲፩ ። ኤጲስቆጶስ ፡ ክንቱ ፡ ውዳሴን ፡ በመፈለግ ፡ ወደሌላው ፡ ሀገረ ፡ ስብከት ፡ ቢመጣ ፡ ሰደቱም ፡ ስለተመቸው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በርሷ ፡ ቢቆይ ፡ የዚያም ፡ አገር ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ያልተማረ ፡ መሆኑን ፡ ቢያውቅ ፡ የአገሩን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሊንቀውና ፡ ሊያቃልለው ፡ አይገባም ። ከካህናትም ፡ ወገን ፡ ክህነትን ፡ ለመቀበል ፡ ለሚፈልጉት ፡ ክህነትን ፡ አይስጥ ። ሰዎቹ ፡ እንዳይንቁት ፡ ቡራኬው ፡ ለበዓለ ፡ መንበር ፡ ይሁን ፡ እንጂ ። ሊሾም ፡ አይገባውም ። ከቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ አይዘግይ ። ፈቃዱን ፡ ለመፈጸም ፡ ከ፫ ፡ ሰንበት ፡ የበለጠ ፡ መሰንበት፡ አይገባውም ። የእጅ ፡ ሥራ ፡ ለማሠራት ፡ ከቦታው ፡ ቢሰነብት ፡ ከሦስት ፡ ሰው ፡ በቀር ፡ ሰው ፡ አያብዛ ።

፻፷፩ ረስጠ፳ ፡ ፸ ። በኤጲስቆጶስ ፡ ላይ ፡ የሐራ ፡ ጥቃን ፡ ምስክርነት ፡ አይቀበሉ ፡ እነርሱም ፡ መናፍቃን ፡ ናቸው ።

፻፷፪ ረስጠብ ፡ ፲፪ ። በርሱ ፡ ላይ ፡ ያንዱን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ምስክርነት ፡ አይቀበሉ ።

፻፷፫ አምስተኛው ፡ ስለ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ መሰብሰብ ፡ ይናገራል ። ይኸውም ፡ በዓመት ፡ ሁለት ፡ ጊዜ፡

ወበእንተእሆሙ ፡ ፪ቱ ፡ ቃላት ።

፻፳፬ ቀዳሚሃ ፡ ረስጠብ ፡ ዘ፳ወ፺ቱ ፡ ረስጠጅ ፡ ዘ፳ወ፰ቱ ፡ ጾክ ፡ ዘ፳ ፡ ወይከውን ፡ ጉባኤ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ፪ቱ ፡ ጊዜ ፡ በበዓመት ፡ ወይትናገሩ ፡ ዘይከውን ፡ በእንተ ፡ ግብረ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያኒሆሙ ፡ ወኵሉ ፡ ዘዐጸበ ፡ ላዕለ ፡ መንፈቆሙ ፡ ፍካሬሁ ፡ ወሥርዓቱ ፡ ወያሰስሉ ፡ ዕቅፋታተ ፡ እለ ፡ ይከውና ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ። ወለእመ ፡ ኮነት ፡ ጽልእ ፡ ይፈጽምዋ ፡ በውናይ ። ወጊዜ ፡ ቀዳሚት ፡ ጉባኤ ፡ በራብዕ ፡ ሰባዔ ፡ እም፶ ፡ ወዳግሚትኒ ፡ አመ ፡ ፲ወ፪ ፡ ለጥምቀት ።

፻፳፭ ወዳግሚታ ፡ ዘኒቅ ፡ ፺ቱ ። ዘኒቅያ ፡ ፺ወ፫ ፡ ይትጋብኡ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ በኵሉ ፡ መካናት ፡ ኀበ ፡ ጳጳሶሙ ፡ አው ፡ ኀበ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቲሆሙ ፡ ፪ቱ ፡ ጊዜ ፡ በኵሉ ፡ ዓመታት ። ቀዳሚ ፡ እምቅድመ ፡ ጾመ ፡ ፵ ፡ በዘይሰስሉ ፡ እኪየ ፡ ወቍጥዓ ፡ ወትኩን ፡ ቍርባኖሙ ፡ በጾም ፡ ቅድስት ፡ ንጽሕተ ፡ ወክብርተ ፡ ለእግዚአብሔር ። ወዳግሚትኒ ፡ በዘመነ ፡ መጸው ፡ እምድኅረ ፡ በዓለ ፡ መስቀል ። እስመ ፡ ይበዝኅ ፡ ሕማመ ፡ ብድብድ ፡ ወሞተ ፡ ግብት ፡ በዘመነ ፡ ሐጋይ ፡ ወተወን ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ፍቅር ፡ ወሰላም ፡ እምቅድመ ፡ ሞት ፡ በዘይበጽሑ ፡ ኀበ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በጽርየት ፡ ወንጽሕ ። ወከመ ፡ ይርአዩ ፡ በእንተ ፡ ፍትሑ ፡ ለዘአውዕአ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እምካህናት ፡ አው ፡ እምካልአኒሆሙ ፡ ከመ ፡ ኢይኩን ፡ ተአንትሎ ፡ አው ፡ በእንተ ፡ ግብር ፡ ዘይከውን ፡ ከማሁ ፡ ወይፍትሑ ፡ በከመ ፡ ይትከሀሎት ፡ ሎሙ ።

፻፳፮ ወለእመ ፡ ተሰወቀ ፡ ፩ዱሂ ፡ እምኔሆሙ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ አእከየ ፡ ላዕለ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ለይትኀሠሥ ፡ ተማኅጸ ፡ ፍጹመ ፡ ፡ ወይትከላእ ፡ እምበዊአ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወትድምርት ፡ እምእመናን ። ወለእመ ፡ ተአዘዘ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ኢይደልዎ ፡ ለዝኩ ፡ ከመ ፡ ይትኀሠሥ ፡ ተማኅፀ ፡ እምነ ፡ ጉባኤ ፡ በእንተ ፡ ኃጢአቱ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ተአመነ ፡ ከመ ፡ ይሥረዩ ፡ ሎቱ ፡ በእንተ ፡ ዘገብረ ፡ ቦቱ ፡ ቂመ ፡ ወመንተ ፡ ወሕሡመ ፡ ያግብእዎ ፡ ኀበ ፡ መዓርጊሁ ፡ ዘቀዳሚ ። ወለእመ ፡ ተቀየመ ፡ ወተምዕዐ ፡ ወተነሥአ ፡ ላዕሌሁ ፡ ለይደቅ ፡ እምዓርጊሁ ።

ነው ። ስለነርሱም ፡ ሁለት ፡ ቃላት ፡ አሉ ።

፻፳፬ መጀመሪያዋ ፡ ረስጠብ ፡ ፳፺ ። ረስጠጅ ፡ ፳፰ ። ጾክ ፡ ፳ ። የኤጲስቆጶሳት ጉባኤ ፡ በዓመት ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ይሁን ። ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናቸው ፡ የሚሆነውን ፡ ሥራ ፡ ይነጋገሩ ። በእኩሌቶቹ ፡ ላይ ፡ ያስቸገረውን ፡ ሁሉ ፡ ትርጓሜውን ፡ ሥርዓቱን ፡ ሁሉ ፡ ይነጋገሩ ። በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ የሚሆኑትንም ፡ መሰናክሎች ፡ ያስወግዱ ። ጠብ ክርክርም ፡ ቢሆን ፡ በዕርቅ ፡ ይፈጽሚት ። መጀመሪያዪቱ ፡ ጉባኤ ፡ በበዓለ ፡ ፶ ፡ በአራተኛው ፡ ሱባኤ ፡ ትሁን ። ሁለተኛዪቱም ፡ ጉባኤ በጥቅምት ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ትሁን ።

፻፳፭ ሁለተኛዋ ፡ ኒቅ ፡ ፺ ። ኒቅያ ፡ ፺፫ ። የየቦታው ፡ ሁሉ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ በየመቱ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ከጳጳሳቸው ፡ ወይም ፡ ከሊቀ ፡ ጳጳሳቸው ፡ ዘንድ ይሰብሰቡ ። መጀመሪያ ፡ ከጾመ ፡ ፵ ፡ በፊት ፡ ይሁን ። ክፉንና ፡ ቍጣን ፡ በሚያርቁ ፡ ገንዘብ ፡ ቍርባናቸውም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ንጽሕት ፡ ክብርት ፡ ቅድስት ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ። ሁለተኛውም ፡ ከበዓለ ፡ መስቀል ፡ በኋላ ፡ በመከር ፡ ወራት ፡ ይሁን ። በበጋና ፡ በበልግ ፡ ወራት ፡ ቸነፈር ፡ የድንገት ፡ ሞት ፡ ይበዛልና ፡ ከሞት ፡ አስቀድሞ ፡ ፍቅር ፡ ሰላም ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ። ወደ ፡ ጌታችን ፡ ወደ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በፍጹም ፡ ንጽሕና ፡ በሚቀርቡ ፡ ገንዘብ ። ከካህናት ፡ ወገን ፡ ወይም ፡ ከሕዝቡ ፡ ወገን ፡ ቢሆን ኤጲስቆጶሱ ፡ አውግዞ ፡ የለየውን ፡ ሰው ፡ ፍርድ ፡ ይመረምሩ ፡ ዘንድ ፡ ቸልታ ፡ እንዳይሆን ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ በሚመስል ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ተገለጠላቸው ፡ ይፈርዱ ፡ ዘንድ ።

፻፳፮ ከነዚህ ፡ አንዱ ፡ ስንኳ ፡ በኤጲስቆጶሱ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ እንደሠራ ፡ ቢታወቅ ፡ ፍጹም ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣ ። ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከመግባት ፡ ከምእመናንም ፡ ጋራ ፡ ከመገናኘት ፡ ይከልከል ። ለኤጲስቆጶሱ ፡ ከታዘዘም ፡ ስለሠራው ፡ ኃጢአት ፡ በጉባኤ ፡ ፍጹም ፡ ቅጣት ፡ ሊቀጣ ፡ አይገባውም ። ስላስቀየመው ፡ ስላስቆጣው ፡ ስላስከፋው ፡ ይቅር ፡ ይሉት ፡ ዘንድ ፡ በደሉን ፡ አምኗልና ፡ ወደቀደመ ፡ ማዕርጉ ፡ ይመልሱት ። ተቀይሞ ፡ ተቆጥቶ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ቢበረታበት ፡ ከማዕርጉ ፡ ይዋረድ ።

## አንቀጽ ፡ ፭ ።

፻፷፯ ድስቅ ፡ ፴ ፡ እመቦ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘተጸውዐ ፡ ኀበ ፡ ዝንቱ ፡ ጉባኤ ፡ ኢያስተቃልል ፡ ሰበጺሕ ፡ ወኢይደኀር ፡ ዘእንበለ ፡ ለእመ ፡ ተጻደቆ ፡ ተመክንዮት ፡ ሰወቅ ፡ ወይጽሐፍ ፡ መልእክተ ፡ እንዘ ፡ ይነግር ፡ ተመክንዮቶ ፡ ወይንግእ ፡ መባሕተ ።

፻፷፰ ዘኒቅያ ፡ ወእምከመ ፡ ተጋብኡ ፡ ኀበ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቲሆሙ ፡ በእንተ ፡ ግብር ፡ ዘይደሉ ፡ ከመ ፡ ይስአልዎ ፡ በእንቲአሁ ፡ ወይፍልጥ ፡ ሎሙ ፡ ፍትሐ ፡ ዘሊአሁ ፡ ወኢይክሥቱ ፡ ምሥጢሮሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘይትፈቀድ ፡ ኀቤሁ ፡ ለከሢት ፡ ዝንቱ ፡ በእንተ ፡ ብዙኅ ፡ እእምሮቱ ፡ ወሃይማኖቱ ፡ ወኢይቁም ፡ ፩ዱሂ ፡ ቅሩበ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ማእምራን ፡ ወያንብሩ ፡ ማእከለ ፡ ምርፋቂሆሙ ፡ ፩ደ ፡ መንበረ ፡ ወያንብርዎ ፡ ዲቤሁ ፡ ለወንጌል ፡ ቅዱስ ። ወይንበር ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በቅድሜሆሙ ፡ ወይሰጽዉ ፡ እናቅጸ ፡ ወይትነሥኡ ፡ ኅቡረ ፡ ወይጸልዩ ፡ ወይግብኡ ፡ ኀበ ፡ ምርፋቆሙ ፡ ወይሕትቱ ፡ በእንተ ፡ ግብር ፡ ዘተጋብኡ ፡ በእንቲአሁ ፡ በኅቡእ ። ወሶበ ፡ ፈጸሙ ፡ ፍትሐ ፡ በተማህሎ ፡ ወፈትሖ ፡ ላዕለ ፡ ዘይደሉ ፡ ላዕሌሁ ፡ ዘንተ ፡ በከመ ፡ ይፈቅድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክሥትዎ ፡ እንከ ።

፻፷፱ ሳድስ ፡ ረስጠጅ ፡ ዘ፸ወ፩ዱ ፡ ዘኒቅያ ፡ ፺ወ፪ቱ ፡ ጳክ ፡ ዘ፳ወ፫ቱ ፡ ኢያወርሱ ፡ ኤጲስቆጶስና ፡ ወኢታበውሕ ፡ ትእዛዝ ፡ በእንቲአሁ ። እስመ ፡ እምላኪዊት ፡ ይእቲ ፡ ኢ ፡ ለዘመድ ፡ ወኢ ፡ ለንክር ፡ ወለከህነትኒ ፡ ከማሁ ።

፻፸ ሳብዕ ፡ ዘኒቅያ ፡ ዘ፶ወ፩ቱ ፡ ኢይሠየሙ ፡ ፪ቱ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ላዕለ ፡ አሐቲ ፡ ሀገር ፡ ወለእመ ፡ ይትጋአዙ ፡ ሰብአ ፡ ሀገር ፡ አው ፡ አህጉር ፡ እስከ ፡ ይትከፈሉ ፡ ኀበ ፡ ፪ቱ ፡ ክፍል ፡ ወበዛቲ ፡ ምክንያት ፡ ተሠይመ ፡ ካልእ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ለይሕትቱ ፡ ጥዩቀ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ። ወለእመኒ ፡ ኢረከቡ ፡ ላዕለ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘይደሉ ፡ ለኰቲሮቱ ፡ ለይንበር ፡ በመካኑ ፡ ወእመሰ ፡ ረከቡ ፡ በላዕሌሁ ፡ ለይሚጦ ፡ በመካን ፡ ዘሊአሁ ፡ ዘአልቦ ፡ ነውር ፡ ውስቴቱ ፡ ወለዝንቱ ፡ ያውግዝዎ ።

፻፸፩ ዶቅ ፡ ዘ፶ወ፪ቱ ፡ ኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ ፪ቱ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ውስተ ፡ አሐቲ ፡ ሀገር ፡ እላ ፡ አብሮኖሮስ ፡ ወውእቱ ፡ ቆሞስ ፡ መትልዉ ፡

## ስለ ፡ ኤጲስቆጶሳት ።

፻፷፯ ድስቅ ፡ ፴ ። ወደዚህ ፡ ጉባኤ ፡ የተጠራ ፡ ኤጲስ ቆጶስ ፡ ቢኖር ፡ አልመጣም ፡ አይበል ። የታወቀ ፡ ምክንያት ፡ ካላገኘው ፡ በቀር ፡ ወደኋላ ፡ አይቅር ። የቀረበትንም ፡ ምክንያት ፡ ይጻፍ ። ፈቃዱም ፡ ይቀበል ።

፻፷፰ ኒቅያ ። ስለሚገባው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ የተሰበሰበበትን ፡ ሥራ ፡ ይጠይቁት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳታቸው ፡ ከተሰበሰቡ ፡ በኋላ ፡ ፍርዱን ፡ ይለይላቸው ። ስለ ፡ እእምሮው ፡ ጽናት ፡ ስለሃይማኖቱም ፡ ምሥጢር ፡ ሊገልጹለት ፡ ለሚገባው ፡ ሰው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለማይገባው ፡ ምሥጢራቸውን ፡ አይግለጡ ። ከአዋቂዎች ፡ በቀር ፡ አንዱ ፡ ስንኳ ፡ ወደነርሱ ፡ ቀርቦ ፡ አይቁም ። በመቀመጫቸውም ፡ መካከል ፡ አንድ ፡ ወንበር ፡ ያኑሩ ። ቅዱስ ፡ ወንጌልንም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ያስቀምጡት ። ሊቀ ፡ ጳጳሳቱም ፡ በፊታቸው ፡ ይቀመጥ ። በሩን ፡ ይዝጉ ። በአንድነት ፡ ተነሥተውም ፡ ይጸልዩ ። በየመቀመጫቸውም፡ ይቀመጡ ። የተሰበሰቡበትንም ፡ ሥራ ፡ በሥውር ፡ (በቆይታ) ፡ ይመርምሩ ። በርኅራኄ ፡ ፍርዱን ፡ በፈጸሙ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደሚወደው ፡ የሚገባውን ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ከፈረዱ ፡ በኋላ ፡ እንግዲህ ፡ ይግለጹለት ።

፻፷፱ ስድስተኛ ፡ ረስጠጅ ፡ ፸፩ ። ኒቅያ ፡ ፺፪ ። ጳክ ፡ ፳፫ ፡ ኤጲስቆጶስነትን ፡ ለሌላ ፡ አያውርሱ ። ሕግ ፡ ስለርሱ ፡ አታዝዝም ፡ የአምላክ ፡ ገንዘብ ፡ ናትና ። ለዘመድም ፡ ለባዕድም ፡ ቢሆን ። ክህነትንም ፡ እንደዚሁ ፡ አያውርሱ ።

፻፸ ሰባተኛ ። ኒቅያ ፡ ፶፩ ። በአንዲት ፡ አገር ፡ ሁለት ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ አይሾሙ ። የከተማና ፡ የገጠር ፡ ሰዎች ፡ ከሁለት ፡ እስከ ፡ መከፈል ፡ ደርሰው ፡ ቢጣሉ ፡ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ሌላ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ቢሾም ፡ ስለዚህ ፡ ፈጽመው ፡ ይመርምሩ ። በፊተኛው ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ላይ ፡ የሚያሽር ፡ ነውር ፡ ካላገኙበት ፡ በቦታው ፡ ይቀመጥ ። በርሱ ፡ ላይ ፡ ቢያገኙበት ፡ ግን ፡ ነውር ፡ የሌለበትን ፡ ይሹሙ ። እርሱን ፡ ግን ፡ ይለዩት ።

፻፸፩ ዶቅ ፡ ፶፪ ። በአንዲት ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ሁለት ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ሊሾሙ ፡ አይገባም ። አብሮኖሮስ ፡ ይኸውም ፡ የኤጲስቆጶሱ ፡ ምክትል ፡ የሚሆን ፡

ለኤጲስቆጶስ ። ወለእመ ፡ ሀለወ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ውስተ ፡ ሀገር ፡ ኢይግበር ፡ ምንተኒ ፡ ቆሞስ ፡ ዘእንበለ ፡ ምክረ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘሀገር ፡ አው ፡ ዘብሔር ።

፻፸፪ ሳምን ፡ ይነግር ፡ በእንተ ፡ ተመክንዮታት ፡ እንተ ፡ ሶበ ፡ ትትዐወቅ ፡ እሐቲ ፡ እምኔሆን፡ በላዕለ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ይወድቅ ፡ እመዓርጊሁ ፡ ወይትመተር ፡ እምሢመቱ ፡ ወኵልቆን ፡ በውስተ ፡ ዝንቱ ፡ አንቀጽ ፡ ፳ወ፰ቱ ፡ ተመክንዮታት ።

፻፸፫ ቀዳሚት ፡ ወዳግሚት ፡ ሣልሲት ፡ ወራብዒት ፡ ዘይነሥእ ፡ ለኤጲስቆጶስና ፡ በሕልያን ፡ አው ፡ በተኀይሎ ፡ አው ፡ በተመይኖ ፡ እው ፡ ዘይሁብ ፡ ኪያሃ ፡ በሕልያን ።

፻፸፬ ረስጠብ ፡ ፳ ፡ ኒቅያ ፡ ፻ወ፫ቱ ፡ በስ ፡ ፵ወ፰ቱ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አው ፡ ቀሲስ ፡ አው ፡ ዲያቆን ፡ ዘይነሥእ ፡ ለዛቲ ፡ መዓርግ ፡ በሕልያን ፡ ይትመተር ። ወዘሤሞሂ ፡ ይትመተር ፡ ወኢይሳተፍዎ ፡ ግሙራ ፡ በከመ ፡ ተገብረ ፡ በሲሞን ፡ መሠርይ ፡ እምኀቤየ ፡ አነ ፡ ጴጥሮስ ።

፻፸፭ ረስጠብ ፡ ፳ወ፩ዱ ፡ ወለእመ ፡ ተራድአ ፡ በመኳንንተ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ወተሠይመ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እምኀቤሆሙ ፡ ይትመተር ፡ ወይሰደድ ፡ ውእቱኒ ፡ ወኵሎሙ ፡ አለ ፡ ተሳተፍዎ ።

፻፸፮ ረስጠጅ ፡ ፳ወ፰ቱ ፡ አው ፡ ዘአስፈወ ፡ ከመ ፡ የሀብ ፡ ሕልያነ ፡ እስከ ፡ ይሠየም ፡ በኍሕሉት ፡ ኢይትወከፉ ፡ ሢመቶ ፡ ወእመኒ ፡ ሞአ ፡ በእንቲአሃ ፡ በኍሕሉት ፡ ምቱር ፡ ውእቱ ፡ ወይኩን ፡ በኀቤክሙ ፡ በአምሳለ ፡ አረማዊ ፡ ወይሰደድ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለእግዚአብሔር ። ወይትገኀሡ ፡ እምተናግሮቱ ፡ ወእምትድምርቱ ፡ በከመ ፡ ተግኀሥኩ ፡ አነ ፡ ጴጥሮስ ፡ አምትድምርተ ፡ ሲሞን ፡ መሠርይ ፡ ወሰደድክዎ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በትእዛዘ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ።

፻፸፯ በስ ፡ ፵ወ፯ቱ ፡ እመሰ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘይነሥእ ፡ ንዋየ ፡ እምነ ፡ ፩ዱ ፡ ዘይሠይሞ ፡ እንዘ ፡ ኢኮነ ፡ ድልወ ፡ ይትወገዝ ፡ ወለዝንቱ ፡ ሲሞን ፡ መሠርይ ፡ ዘዘከርዎ ፡ ሐዋርያት ፡ በቀኖናሆሙ ፡ ውእቱ ፡ ዘዘከሮ ፡ ሉቃስ ፡ በመጽሐፈ ፡ አብረክሲስ ፡ ወይቤ ፡ ወሶበ ፡ ርእየ ፡ ሲሞን ፡ ከመ ፡ በአንብሮ ፡ እደዊሆሙ ፡ ለሐዋርያት ፡ ይወ

ቆሞስ ፡ ነው ፡ ቆሞሱ ፡ ይሁን፡ እንጂ ። ኤጲስቆጶሱ ፡ በአገር ፡ ያለ ፡ እንደሆነ ፡ ቆሞሱ ፡ ያለ ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ ፈቃድ ፡ በከተማ ፡ ወይም ፡ በገጠር ፡ ምንም ፡ አይሥራ ።

፻፸፪ ስምንተኛው ፡ ከነውር ፡ ወገን ፡ አንዲቱ ፡ ነውር በኤጲስቆጶስ ፡ ላይ ፡ ብትታወቅበት ፡ ከመዓርጉ ፡ የሚዋረድበትን ፡ ከሹመቱ ፡ የሚሻርበትን ፡ ምክንያት ፡ ይናገራል ። በዚህም ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ ቍጥራቸው ፡ ፳፰ ፡ ምክንያቶች፡ ናቸው ።

፻፸፫ መጀመሪያዋና ፡ ሁለተኛዋ ፡ ሦስተኛዋና ፡ አራተኛዋ ፡ ኤጲስቆጶስነትን ፡ በማማለጃ ፡ በጉልበት ፡ በተንኰል ፡ ስለ ፡ ተሾመው ፡ ወይም ፡ ማማለጃ ፡ ተቀብሎ ፡ ስለሾመው ፡ ነው ።

፻፸፬ ረስጠብ ፡ ፳ ። ኒቅያ ፡ ፻፫ ። በስ ፡ ፵፰ ። ይህችን ፡ ማዕርግ ፡ በማማለጃ ፡ የተሾመ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወይም ፡ ቄስ ፡ ወይም ፡ ዲያቆን ፡ ይሻር ። የሾመውም ፡ ይሻር ። በእኔ ፡ በጴጥሮስ ፡ ዘንድ ፡ በመሠርዩ ፡ በሲሞን ፡ ላይ ፡ እንደተደረገው ፡ ፈጽመው ፡ አይገናኙት ።

፻፸፭ ረስጠብ ፡ ፳፩ ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ መኳንንት ፡ ቢረዳ ፡ ከነርሱም ፡ ዘንድ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቢሾም ፡ ይሻር ። እርሱና ፡ ግብረ ፡ አበሮቹ ፡ ሁሉ ፡ ይለዩ ።

፻፸፮ ረስጠጅ ፡ ፳፰ ። ወይም ፡ እስኪሾም ፡ ድረስ ፡ መማለጃ ፡ እሰጣለሁ ፡ ብሎ ፡ የተሾመ ፡ ሹመቱን ፡ አይቀበሉት ። በተንኰል ፡ቢያሸንፍም ፡ የተለየ ፡ ነው ። በእናንተም ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ አረማዊ ፡ ይሁን ። ከእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ይለይ ። ከርሱ ፡ ጋር ፡ ከመነጋገርና ፡ ከመገናኘት ፡ ይራቁ ። እኔ ፡ ጴጥሮስ ፡ ከሲሞን ፡ መሠርይ ፡ ጋር ፡ ከመገናኘት ፡ እንደራቅሁ ። በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ትእዛዝ ፡ ከእግዚአብሔር ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደ ፡ ለየሁት ።

፻፸፯ በስ ፡ ፵፯ ። ሳይገባው ፡ ገንዘብ ፡ ተቀብሎ ፡ የሚሾም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ቢኖር ፡ ይለይ ። ሐዋርያት ፡ በመጽሐፋቸው ፡ የጻፉት ፡ ሉቃስም ፡ በግብረ ፡ ሐዋርያት ፡ የጻፈው ፡ ሲሞን ፡ መሠርይ ፡ ነው ። (የሐዋ ፡ ሥራ ፡ ፰ ፡ ፲፰ - ፲፱) ። ሲሞን ፡ ሐዋርያት ፡ እጃቸውን በጫኑበት ሰው ፡ ላይ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሲወርድበት ባየ ፡ ጊዜ ፡ መን

ርድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አምጽአ ፡ ሎሙ ፡ ንዋየ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ሀቡኒ ፡ ሊተኒ ፡ ዘንተ ፡ ሥልጣነ ፡ ከመ ፡ ሶበ ፡ አንበርኩ ፡ እደየ ፡ ይረድ ፡ ላዕሌሁ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ። ወይቤሎ ፡ ስምዖን ፡ ብሩርከ ፡ ትሑር ፡ ምስሌከ ፡ ውስተ ፡ ኀጕል ፡ በእንተ ፡ ዘሐለይከ ፡ አንተ ፡ ከመ ፡ ሀብተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በረባሕ ፡ ዓለም ፡ ትጠሪ ፡ አልብከ ፡ ክፍል ፡ ወኢርስት ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ሃይማኖት ። እስመ ፡ ልብከ ፡ ኢኮነ ፡ ርቱዐ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጻእሙ ፡ ተመየጥ ፡ እምዝንቱ ፡ እከይከ ፡ ወስአል ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ይሥረይ ፡ ለከ ፡ ውእቱ ፡ እከየ ፡ ልብከ ።

፻፸፭ ኃምስ ፡ ረስጠጅ ፡ ፳ወ፱ቱ ፡ እመቦ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘተማኅፀነ ፡ በእንተ ፡ ምግብናሁ ፡ ለስብእ ፡ እፉእ ፡ አው ፡ በመኳንንተ ፡ ዓለም ፡ ከመ ፡ ይርድእዎ ፡ በእንተ ፡ ሥርዓተ ፡ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዘ ፡ የኀሥሥ ፡ በዝንቱ ፡ አኀስሮቶሙ ፡ ለሕዝበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወከመ ፡ ይትዐበይ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ በዘኢይደሉ ፡ አው ፡ ከመ ፡ ይማዕ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ካልአ ፡ ውጉዝ ፡ ውእቱ ፡ ወምቱር ፡ ወኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይትራድእዎ ፡ በዝንቱ ፡ ግብር ።

፻፸፮ ሳድስ ፡ በስ ፡ ዘ፲ወ፰ቱ ፡ እመቦ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘይነሥእ ፡ ሕልያነ ፡ እምቀሳውስት ፡ ወዲያቆናት ፡ ወየኀድጎሙ ፡ ኀበ ፡ መዓርጊሆሙ ፡ እንዘ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ፍትሕ ፡ ለይሣእ ።

፻፸፯ ሳብዕ ፡ ጳክ ፡ ዘ፲ወ፯ቱ ፡ እመቦ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አው ፡ ጳጳስ ፡ አው ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እስመ ፡ በእንቲአሆሙ ፡ አሐቲ ፡ ፍኖት ፡ ዘአበየ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እምድኅረ ፡ ሢመቱ ፡ ወተወክፎቱ ፡ እሎንተ ፡ መዓርጋተ ፡ ወለእመኒ ፡ አሐደ ፡ ዕለተ ፡ አው ፡ አሐተ ፡ ሰዓተ ፡ ወእምዝ፡ ኀዶየ ፡ እምውእቱ ፡ መንበር ፡ ይትወቀሥ ፡ እምሰብአ ፡ ሀገሩ ፡ እስከ ፡ አሆ ፡ ይበል ፡ ወይትመየጥ፡ ኀበ ፡ መንበሩ ፡ ወእመ ፡ አኮ ፡ ይስደድ ፡ እምነ፡ መካን ፡ ዘፈተወ ፡ ይንበር ፡ ውስቴቱ ፡ ወእምተደምሮ ፡ ጉባኤ ። ወእመ ፡ ኢተመይጠ ፡ ድኅረ ፡ ሰአልዎ ፡ ሰብአ ፡ ሀገሩ ፡ ኅሪየተ ፡ ሎሙ ፡ እመ ፡ ፈቀዱ ፡ ያንብርዎ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ወይገዝኩ ፡ ስሞ ። ወለእመሰ ፡ ጸልእዎ ፡ ኢይገዝኩ ፡ ስሞ ፡ እስመ ፡ ይደሉ ፡ ይጸልዩ ፡ ላዕሌሁ ፡ በከመ ፡ ውእቱ ፡ ጸለየ ፡ ላዕሌሆሙ ።



ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ያድርበት ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ ሥልጣን ፡ ስጡኝ ፡ ብሎ ፡ ገንዘብ ፡ አመጣላቸው ። ስምዖንም ፡ አለው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ጥቅም ፡ ሀብተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ገንዘብ ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ ስላሰብህ ፡ ብርህ ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ ለጥፋትህ ፡ ትሁን ። በዚህ ፡ ሃይማኖት ፡ ውስጥ ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ ርስትም ፡ የለህም ። ልብህ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የቀና ፡ አይደለምና ፡ ከዚህ ፡ ክፋትህ ፡ ተመለስ ፡ እንጂ ፡ እርሱ ፡ የልብህን ፡ ክፋት ፡ ያስተሠርይልህ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለምን ።

፻፸፭ አምስተኛ ። ረስጠጅ ፡ ፳፱ ። እሾምሃለሁ ፡ ብሎ፡ ከውጭ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ወይም ፡ ከዓለም ፡ መኳንንት ፡ ጋር ፡ ስለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሹመት ፡ ይረዱት ፡ ዘንድ ፡ የተማፀነ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ቢኖር ፡ በዚህ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ሕዝብ ፡ ሊያዋርድ ፡ በማይገባ ፡ በላያቸው ፡ ሊታበይ ፡ ወይም ፡ የባልንጀራውን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሊወስድ ፡ ፈልጎ ፡ የተማፀነ ፡ ቢኖር ፡ ፈጽሞ ፡ የተወገዘ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ሥራ ፡ የሚረዱትም ፡ ሁሉ ፡ ፈጽመው ፡ የተወገዙ ፡ ናቸው ።

፻፸፮ ስድስተኛ ። በስ ፡ ፲፰ ። ከቀሳውስትና ፡ ከዲያቆናት ፡ መማለጃ ፡ ተቀብሎ ፡ ፍርድ ፡ እያለባቸው ፡ በመዓርጋቸው ፡ የሚተዋቸው ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ቢኖር ፡ ይሻር ።

፻፸፯ ሰባተኛ ፡ ጳክ ፡ ፲፯ ። ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወይም ፡ ጳጳስ ፡ ወይም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ቢሆን ፡ ስለነርሱ ፡ሕግ ፡ አንዲት ፡ ናትና ፡ ከተሾመና ፡ እኒህን ፡ መዓርጋት ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ አንዲት ፡ ዕለት፡ ወይም ፡ አንዲት ፡ ሰዓትም ፡ ቢሆን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ያላገለገለ ፡ ቀጥሎም ፡ የተሾመበትን ፡ አገር ፡ ጥሎ ፡ የሸሸ ፡ ቢኖር ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ ወደ ቦታው ፡ እስኪመለስ ፡ ድረስ ፡ የአገሩ ፡ ሰዎች ፡ ይማልዱት ። አልመለስም ፡ ቢል ፡ ሊኖር ፡ ከሄደበት ፡ አገርና ፡ ከምእመናን ፡ ጉባኤ ፡ ይለይ ። የአገሩ ፡ ሰዎች ፡ ከለመኑት ፡ በኋላ ፡ ባይመለስ ፡ በእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ እንዲኖር ፡ ስሙንም ፡ ሊጠሩት ፡ ቢወዱ ፡ ምርጫ ፡ አላቸው ። ቢጠሉት ፡ ግን ፡ ስሙን ፡ አይጥሩ ። እርሱ ፡ ስነርሱ ፡ እንደ ጸለየ ፡ እነርሱም ፡ ይጸልዩበት ፡ ዘንድ ፡ ይገባልና ።

አንቀጽ ፡ ፭ ።

፻፹፩ ሳምን ፡ ወታስዕ ፡ ረስጠብ ፡ ዘሣወጺቱ ፡ እመቦ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አው ፡ ቀሲስ ፡ አው ፡ ዲያቆን ፡ ዘተሠይመ ፡ ፪ተ ፡ ጊዜ ፡ ይትመተር ፡ ውእቱኒ ፡ ወዘሤሞ ። እላ ፡ ለእመ ፡ አያቀ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ዘተሠይመ ፡ እምኅበ ፡ ሐራ ፡ ጥቃ ። ረስጠጅ ፡ ዘ፸ወ፪ቱ ፡ ወከማሁ ፡ ለእመ ፡ አውሰበ ፡ ፪ተ ፡ አንስተ ፡ እምቅድመ ፡ ሢመቱ ፡ ወተሠይመ ፡ ይትመተር ፡ ውእቱሂ ፡ ወዘሤሞ ፡ እላ ፡ ባሕቱ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ውእቱ ፡ ዘኢይደመር ፡ ግብሩ ፡ ይትመተር ፡ ውእቱ ፡ ባሕቲቱ ።

፻፹፪ ዓሥር ፡ ዘኒቅያ ፡ ፴ወ፰ቱ ፡ እመቦ ፡ ኤጲስቆጶስ፡ ዘኮነ ፡ ተቀያሚ ፡ ፈድፋደ ፡ አው ፡ ዘያፈጥን ፡ ቍጥዓ ፡ እስከ ፡ ውእቱ ፡ የአሥር ፡ ወያወግዝ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ ወኢየኀድግ ፡ ዘንተ ፡ ወዘያፈቅር፡ ክብረ ፡ ወኢየኀድግ ፡ ቂመ ፡ ከመ ፡ ያፋጥን ፡ ግዘተ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ ይደቅ ፡ እመዓርጊሁ ፡ ወከማሁ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይመስልዎ ፡ ይኩኑ ፡ ውጉዛነ ።

፻፹፫ ድስቅ ፡ ዘ፲ቱ ፡ ወኤጲስቆጶስ ፡ ዘድልው ፡ ለፍትሕ ፡ እመ ፡ ፈትሐ ፡ በዐመፃ ፡ ላዕለ ፡ ፩ዱኒ ፡ እስመ ፡ ፍትሕ ፡ ዘይወዕእ ፡ እምእፉሁ ፡ ላዕለ ፡ ነፍሱ ፡ ውእቱ ።

፻፹፬ ረስጠብ ፡ ዘ፳ወ፱ቱ ፡ ወይኩን ፡ ሊቅ ፡ ዘይኄሥሮሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ወየአስሮሙ ፡ በመስቀል ፡ አኮ ፡ በግዘት ፡ ኢያእሥር ፡ ወኢያውግዝ ፡ ዘእንበለ ፡ ርትዕ ። ወለእመሰ ፡ ውእቱ ፡ እሠረ ፡ ወአውገዘ ፡ ዘእንበለ ፡ ርትዕ ፡ እንዘ ፡ የኀሥሥ ፡ ከመ ፡ ያተክዞሙ ፡ ለሰብእ ፡ ወይፈቅድ ፡ ስሕተቶሙ ፡ ወተጋንዮቶሙ ፡ ሎቱ ፡ ይኩን ፡ ውእቱ ፡ እሡረ ፡ ወውጉዘ ፡ እምኅበ ፡ እግዚአብሔር ። ወይቀሥሙ ፡ ላዕሌሁ ፡ ካህናቲሁ ፡ በጽድቅ ፡ ዘይደሉ ።

፻፹፭ ወለእመ ፡ ጸንዐ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ግብሩ ፡ ያጠይቁ፡ ግብሮ ፡ ኀበ ፡ ጳጳሱ ፡ አው ፡ ኀበ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቲሁ ፡ ወይትነሥኡ ፡ ላዕሌሁ ፡ በጽድቅ ፡ ወኢይኅድግዎ ፡ ይትበየው ፡ ኀበ ፡ አባግዐ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘተሣየጦሙ ፡ በደሙ ፡ ወኢያስተቀኑጥዎሙ ፡ ወኢያብጽሑሙ ፡ ኀበ ፡ ዕርፈት ፡ ላዕለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወከሂደ ፡ ሕጉ ፡ ቅድስት ። ወኢይኅድግዎ ፡ ይንበር ፡ ላዕለ ፡ ፍትሕ ፡ ወኢየአገዝዝ ፡ በሢመቱ ፡ ወይኩን ፡ መሃይምነ ፡ እንዘ ፡ ይትዌከፍ ፡ ግፍዖ ፡ በሠናይ ፡ ከመ ፡ ዘይደሉ ፡ ላዕሌሁ ።

ስለ ፡ ኤጲስቆጶሳት ።

፻፹፩ ስምንተኛና ፡ ዘጠኛኛ ። ረስጠብ ፡ ፸፪ ። ሁለት፡ ጊዜ ፡ የተሾመ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወይም ፡ ቄስ ፡ ወይም ፡ ዲያቆን ፡ ቢኖር ፡ ይሻር ፡ ሿሚውም ፡ ይሻር ። ከሐራ ፡ ጥቃ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ተሾመ ፡ ቢያስረዳ ፡ ግን ፡ አይሻርም ። ረስጠጅ ፡ ፸፪ ። እንደዚሁም ፡ ከሹመቱ ፡ በፊት ፡ ሁለት ፡ ሚስት ፡ አግብቶ ፡ የተሾመ ፡ ቢኖር ፡ እርሱም ፡ ሿሚውም ፡ ይሻር ። ሥራው ፡ የታወቀ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ ይሻር ።

፻፹፪ አሥረኛ ፡ ኒቅያ ፡ ፴፰ ። ፈጽሞ ፡ ቂመኛ ፡ የሆነ ፡ ወይም ፡ በየጊዜው ፡ ሁሉን ፡ እስከ ፡ ማሠርና ፡ እስከ ፡ ማውገዝ ፡ ድረስ ፡ ፈጥኖ ፡ የሚቆጣ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ቢኖር ፡ ይህን ፡ ባይተው ፡ ክብ ርን ፡ የሚወድ ፡ ሁልጊዜ ፡ ፈጥኖ ፡ ስማውገዝ ፡ ቂሙን ፡ የማይረሳ ፡ ቢሆን ፡ ከሹመቱ ፡ ይሻር ። እርሱንም ፡ የሚመስሉት ፡ ሁሉ ፡ የተለዩ ፡ ይሁኑ ።

፻፹፫ ድስቅ ፡ ፲ ። ለፍርድ ፡ የተዘጋጀ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ ስንኳ ፡ በሐሰት ፡ ቢፈርድ ፡ በፈረደው ፡ ፍርድ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ይፈረድበ ታል ።

፻፹፬ ረስጠብ ፡ ፳፱ ። አለቃው ፡ ሕዝቡን ፡ የሚመክ ራቸው ፡ በውግዘት ፡ ያይደለ ፡ በመስቀል ፡ የሚ ያሥራቸው ፡ ይሁን ። በማይገባ ፡ አያውግዝ ። ሰዎችን ፡ ሊያሳዝናቸውና ፡ ፈርተው ፡ እንዲገ ዙለት ፡ ፈልጎ ፡ በማይገባ ፡ ቢያሥር ፡ ቢያወግዝ እርሱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የታሠረ ፡ የተ ወገዘ ፡ ይሁን ። ካህናትም ፡ በእውነት ፡ ይቋቋ ሙት ።

፻፹፭ ግብሩ ፡ ቢጸናባቸው ፡ ግብሩን ፡ ወደ ፡ ጳጳሱ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ አቅርበው ፡ ያስረዱ ። በእውነት ፡ ይነሡበት ። ክርስቶስ ፡ በደሙ ፡ የዋጃቸውን ፡ ምእመናንን ፡ ይበድ ላቸው ፡ ዘንድ ፡ አይተውት ። አያስቈጣ ቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ወደ ፡ መሳደብና ፡ ቅድስት ፡ ሕጉን ፡ ወደ ፡ መካድ ፡ እያደርሳ ቸው ። በሹመቱ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ አይተውት ። በሹመትም ፡ አይዘዝ ። ለርሱ ፡ እንደሚገባው ፡ በደሉን ፡ ተቀብሎ ፡ በሚገባ ፡ መሃይምን ፡ ይሁን ።

፻፹፮ ወይኩን ፡ ውእቱ ፡ ዘይትነሣእ ፡ እግዚአብሔር፡ በግፍዐ ፡ ዚአሁ ። ወኢይኅድግዎ ፡ ሰብአ ፡ ፈታሕያን ከመ ፡ ይትመየጥ ፡ ኀበ ፡ ስሕተቱ ። ወሕዝብኒ ፡ ይኩኑ ፡ ተወካፍያን ፡ አበሳሁ ፡ ለሠንዮቱ ፡ በከመ ፡ ግብር ፡ ዘድልው ፡ ሎቱ ፡ ውእቱኒ ፡ ይኩን ፡ አስተብቋዔ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ አበሳሁ ።

፻፹፯ ዓሥር ፡ ወ፩ዱ ፡ ረስጠጅ ፡ ዘ፶ወ፪ቱ ፡ ረስጠብ ፡ ፶ወ፩ ፡ ረስጠብ ፡ ዘ፳ወ፯ቱ ፡ ዘ፴ወ፰ቱ ፡ ኤጲስ ቆጶስ ፡ አው ፡ ቀሲስ ፡ አው ፡ ዲያቆን ፡ ዘይትሀ ከይ ፡ እምትምህርተ ፡ ካህናቲሁ ፡ ወሕዝቡ ፡ ወተልእኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወፈራሆቱ ፡ ይት ፈለጥ ፡ ወእመ ፡ አዝለፈ ፡ ነቢረ ፡ በሀኬቱ ፡ ይትመተር ።

፻፹፰ ጀ ፡ ፺ቱ ፡ ወከመዝ ፡ እግዚእነ ፡ አቅደመ ፡ ከመ፡ ይግበር ፡ ወይምሀር ፡ ሉቃስ ፡ ይቤ ፡ እስመ ፡ ኵሎሙ ፡ ሐዋርያት ፡ ኮኑ ፡ ይፀመዱ ፡ ኵሎ ፡ ዕለተ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ወምኵራብ ፡ በእንተ ፡ ትምህርት ፡ ወበከመ ፡ አዘዘ ፡ ጳውሎስ ፡ ለረድኡ ፡ ከመ ፡ ያዝልፍ ፡ በእንተ ፡ ትምህርት ።

፻፹፱ ዓሥር ፡ ወካልእ ፡ ረስጠብ ፡ ፶ወ፱ቱ ፡ ረስጠብ ፡ ፷ ፡ እመቦ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አው ፡ ቀሲስ ፡ ዘይትኄየዮሙ ፡ ለካህናት ፡ ወለነዳያን ፡ ወኢይሁቦሙ ፡ በዘይትከሀሎ ፡ ይትፈለጥ ፡ ወለእመ ፡ አዝለፈ ፡ በተኀይዮቱ ፡ ይትመተር ፡ ከመ ፡ ቀታሌ ፡ እኑሁ ።

፻፺ ዓሥር ፡ ወሣልስ ፡ ረስጠብ ፡ ፷ወ፫ቱ ፡ ረስጠጅ ፡ ፷ወ፪ቱ ፡ እመቦ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አው ፡ ቀሲስ ፡ ዘኢይትዌከፍ ፡ ለኃጥእ ፡ ሶበ ፡ ነስሐ ፡ ይትመተር ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ተሀየደ ፡ ዘይቤ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ይከውን ፡ በሰማያት ፡ ፍሥሓ ፡ ብዙኀ ፡ በእንተ ፡ ፩ዱ ፡ ኃጥእ ፡ ዘይኔስሕ ። ጀ ፡ ፺ቱ ፡ ወእግዚእነሰ ፡ ኢመጽአ ፡ ከመ ፡ ይጸውዕ ፡ ጻድቃነ ፡ አላ ፡ ኃጥአነ ፡ ለንስሓ ።

፻፺፩ አሥር ፡ ወራብዕ ፡ ረስጠብ ፡ ዘ፷ወ፩ዱ ፡ እመቦ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አው ፡ ቀሲስ ፡ አው ፡ ዲያቆን ፡ ዘኮነ ፡ መዝለፈ ፡ ስካር ፡ ወእከይ ፡ ለንዲገ ፡ ሠና ይት ፡ ፷ወ፪ቱ ፡ አው ፡ ኀሠሠ ፡ እምነ ፡ ዘይፈ



፻፹፮ በበደሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚመረምረው ፡ ይሁን ። ወደ ፡ በደሉ ፡ ይመለስ ፡ ዘንድ ፡ ፈራ ጆች ፡ ሰዎች ፡ አይተውት ። ሕዝቡም ፡ ለርሱ ፡ እንደሚገባ ፡ ለበጎ ፡ ሥራ ፡ በደሉን ፡ ይቅር ፡ የሚሉት ይሁኑ ። እርሱም ፡ ስለ ፡ በደሉ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚማልድ ፡ ይሁን ።

፻፹፯ አሥራ ፡ አንደኛ ። ረስጠጅ ፡ ፶፪ ። ረስጠብ ፡ ፶፩ ። ረስጠብ ፡ ፳፯ ፡ ፴፰ ። እግዚአብሔርን ፡ ከማገልገልና ፡ ከመፍራት ፡ ሕዝቡንና ፡ ካህና ቱንም ፡ ከማስተማር ፡ ቸል ፡ የሚል ፡ ኤጲስ ቆጶስ ፡ ወይም ፡ ቄስ ፡ ወይም ፡ ዲያቆን ፡ በስን ፍናው ፡ ጸንቶ ፡ ቢኖር ፡ ይሻር ።

፻፹፰ ጀ ፡ ፺ ። እንደዚህም ፡ ጌታችን ፡ ሥራውን ፡ አስቀድሞ ፡ ሠርቶ ፡ ማስተማር ፡ ጀመረ ። (የሐ ዋ ፡ ፩ ፡ ፩-፪) ። ሉቃስም ፡ ሐዋርያት ፡ ሁሉ ፡ ለማስተማር ፡ ሁልጊዜ ፡ በምኵራብና ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ያገለግሉ ፡ ነበር ፡ አለ ። (የሐዋ ፡ ፲፫ ፡ ፩- ፪) ። ጳውሎስም ፡ ደቀመዝሙሩን ፡ ዘወ ትር ፡ ያስተምር ፡ ዘንድ ፡ እንዳዘዘው ። (፪ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፩ -፪) ።

፻፹፱ አሥራ ፡ ሁለተኛ ። ረስጠብ ፡ ፶፱ ። ረስጠብ ፡ ፷ ። ድሆችንና ፡ ካህናትን ፡ ቸል ፡ የሚላቸው ፡ የሚቻለውንም ፡ የማይሰጣቸው ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወይም ፡ ቄስ ፡ ቢኖር ፡ ይለይ ። ቸል ፡ በማለት ፡ ጸንቶ ፡ ቢኖርም ፡ ወንድሙን ፡ ገዳይ ፡ እንደመ ሆኑ ፡ ይሻር ።

፻፺ አሥራ ፡ ሦስተኛ ። ረስጠብ ፡ ፷፫ ። ረስጠጅ ፡ ፷፪ ። ንስሓ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ኃጢአተኛውን ፡ የማ ይቀበል ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወይም ፡ ቄስ ፡ ቢኖር ፡ ይሻር ፡ ንስሓ ፡ ስለሚገባ ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ ኃጢ አተኛ ፡ በሰማይ ፡ ፍጹም ፡ ደስታ ፡ ይሆናል ፡ (ሉቃ ፡ ፲፭ ፡ ፯) ። ብሎ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የተናገረውን ፡ አፍርሷልና ። ጀ ፡ ፺ ። ጌታችን ፡ ግን ፡ ጻድቃንን ፡ ሊጠራ ፡ አልመጣም፡ ኃጥአንን ፡ ለንስሓ ፡ ሊጠራ ፡ መጣ ፡ እንጂ ። (ማቴ ፡ ፱ ፡ ፲፫) ።

፻፺፩ አሥራ ፡ አራተኛ ። ረስጠብ ፡ ፷፩ ። መልካሞን ፡ ለመተው ፡ ስካርንና ፡ ክፋትን ፡ የሚያዘወትር ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወይም ፡ ቄስ ፡ ወይም ፡ ዲያቆን ፡ ቢኖር ። ፷፪ ፡ ወይም ፡ ከአበደረው ፡ ሰው ፡

ድዮ ፡ ነሚእ ፡ ርደ ። ጼጥ ፡ ዘ፲ወ፰ቱ ፡ እው ፡
ኮነ ፡ ሰማዕተ ፡ ሐሰት ፡ ወመስተዋድየ ፡ ለሰ
ብእ ፡ ዘ፳ወ፬ቱ፡ እው ፡ ገብረ ፡ ትዕቢተ ፡ ላዕለ ፡
ሰብእ ፡ ወይሬሊ ፡ ርእሶ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ዐቢይ ፡
እምኔሆሙ ፡ ወይሬእዮሙ ፡ ለሕዝበ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ በዓይን ፡ ሕፀፅት ፡ ኢይከውን ፡ ሎቱ ፡
ዝክር ፡ ሠናይ ፡ በሕይወቱ ፡ ወኢምሕረት ፡ እም
ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምድኅረ ፡ ሞቱ ።

፻፶፪ ዘ፲ወ፺ቱ ፡ ኢይኩን ፡ ሊቀ ፡ ላዕለ ፡ ክርስቲያን ፡
ወኢይአመንዎ ፡ በሥርዓታቲሃ ፡ አንበለ ፡ ዘየእ
ምር ፡ ሕገጋቲሃ ፡ ወቀኖናቲሃ ፡ ወዘይገብር ፡
ቦሙ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ተዓዳዌ ፡ ለዝንቱ ፡ ይሠ
ዐር ፡ እምኑ ፡ ሢመቱ ፡ በግብር ።

፻፶፫ ዘኒቅያ ፡ ዘ፲ወ፱ቱ ፡ ይስደድ ፡ ወይትከላእ ፡
ዘይስክብ ፡ ብእሲተ ፡ እረማዊተ ፡ እው ፡ ዘማ
ዊተ ፡ ወኢይሳተፎን ፡ ከመ ፡ ኢይሕፅፅ ፡ ሃይ
ማኖተ ፡ ምእመናን ፡ ወካህናት ። ወዓዲ ፡ ይር
ኅቅ ፡ እምተደምሮ ፡ እዕርክታት ፡ ዘተሐበየ ፡
ውሉዶን ፡ በክርበትና ፡ እስመ ፡ ዲያብሎስ ፡
መስተቃርን ፡ ይትቃተሎሙ ፡ ለክርስቲያን ፡
ወፈድፋደሰ ፡ ለሥዩማኒሆሙ ፡ በእንተ ፡ ምሂሮ
ቶሙ ፡ ወቀሪቦቶሙ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡
ወየኀሥሥ ፡ አርኅቆቶሙ ፡ እምኔሁ ፡ ወእምነ ፡
መዓርገ ፡ ክህነቶሙ ።

፻፶፬ ዓሥር ፡ ወኃምስ ፡ ረስጣ ፡ ፴ወ፬ቱ ፡ ረስጠጅ ፡
፳ወ፬ቱ ፡ እመቦ ፡ ዘሤመ ፡ ካህነ ፡ በእፍአ ፡
እምስብከተ ፡ መንበሩ ፡ እንበለ ፡ ምክረ ፡ በዓለ ፡
መንበሩ ፡ ይትመተር ።

፻፶፭ ጳክ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ወለእመ ፡ በጽሐ ፡ ኀበ ፡ ሀገር ፡
ካልእ ፡ እንዘ ፡ የኀልፍ ፡ እው ፡ እንዘ ፡ ይፈቅድ ፡
ከመ ፡ ይኩን ፡ በሀየ ፡ ቀሲስ ፡ እው ፡ ዲያቆነ ፡
ኢይደሉ ፡ ለእመ ፡ ኢኮነ ፡ ምስሌሁ ፡ ኤጲስ
ቆጶስ ፡ ዘመጽእ ፡ ወእመ ፡ እኮ ፡ አመ ፡ ኢጸሐፉ
ሎቱ ፡ ጳጳስ ፡ ወኤጲስቆጳሳት ፡ ዘሀገሩ ፡ ወሶበ ፡
ገብረ ፡ ዘንተ ፡ በምክረ ፡ ነፍሱ ፡ ይጸራዕ ፡ ክህነ
ቶሙ ፡ ለእለ ፡ ሤሞሙ ፡ ወውእቱሂ ፡ ይትመ
ተር ፡ እመዓርጊሁ ።

፻፶፮ ዓሥር ፡ ወሳድስ ፡ በስ ፡ ፴ወ፰ቱ ፡ ወለእመ ፡
ሰደዶ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ለ፩ዱ ፡ ካህን ፡ ወአብእ ፡
ኀቤሁ ፡ ካልእ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እንዘ ፡ የአምር ፡
ግብሮ ፡ ይትመተር ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወለእመ ፡
አውፅእዎ ፡ ካህናት ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ዘርቱዕ ፡
ግብሩ ፡ ወሤሙ ፡ ካልእ ፡ ህየንቴሁ ፡ ይትመ



እራጣ ፡ የሚቀበል ። ጼጥ ፡ ፲፰ ። ወይም ፡ በሐ
ሰት ፡ ቢመሰክር ፡ ሰውንም ፡ ቢያጣላ ። ጼጥ ፡
፳፬ ። ወይም ፡ በሰዎቹ ፡ ላይ ፡ ቢታበይ ፡ ከነ
ርሱ ፡ ራሱን ፡ ታላቅ ፡ ቢያደርግ ። የእግዚአብ
ሔርንም ፡ ሕዝብ ፡ እቈልቍሎ ፡ ቢያያቸው ፡
በሕይወተ ፡ ሥጋው ፡ ሳለ ፡ መልካም ፡ ስም ፡
አይሆንለትም ። ከሞተም ፡ በኋላ ፡ በእግዚእ
ብሔር ፡ ዘንድ ፡ ይቅርታ ፡ አይደረግለትም ።

፻፶፪ ፲፺ ፡ ጼጥ ። በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ላይ ፡ አስተዳ
ዳሪ ፡ አይሁን ። በሥርዓትዋም ፡ አይመኑት ።
ሕግዋንና ፡ ሥርዓትዋን ፡ የሚያውቅ ፡ የሚ
ሠራቸውም ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ። ይህን ፡ የተደፋ
ፈረ ፡ ቢሆንም ፡ በግድ ፡ ከሹመቱ ፡ ይሻር ።

፻፶፫ ኒቅያ ፡ ፲፱ ። አረማዊቱን ፡ ወይም ፡ ዘማዊቱን ፡
ሴት ፡ የተኛ ፡ ይለይ ፡ ይከልከል ። የክርስቲያን ፡
ሃይማኖትና ፡ የካህናት ፡ መዓርግ ፡ እንዳይነቀፍ
አይገናኛቸው ። ዳግመኛም ፡ በክርስትና ፡ ልጃ
ቸውን ፡ ካነሣላቸው ፡ ሴቶች ፡ ከመገናኘት ፡
ይራቅ ። ባላጋራ ፡ ዲያብሎስ ፡ ክርስቲያኖችን ፡
ይዋጋቸዋልና ። ይልቁንም ፡ ስለማስተማራቸ
ውና ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለመቅረባቸው ፡
ሹማምንቱን ፡ ይዋጋቸዋልና ። ከእርሱና ፡ ከክ
ህነታቸው ፡ ማዕርግ ፡ ሊያርቃቸውም ፡ ይፈል
ጋል ።

፻፶፬ አሥራ ፡ አምስተኛ ። ረስጣ ፡ ፴፬ ። ረስጠጅ ፡
፳፬ ። ባለ ፡ ሀገረ ፡ ስብከቱ ፡ ሳይፈቅድለት ፡
ከሀገረ ፡ ስብከቱ ፡ ውጪ ፡ ካህንን ፡ የሾመ ፡
ቢኖር ፡ ይሻር ።

፻፶፭ ጳክ ፡ ፲፪ ። አልፎ ፡ ሲሄድ ፡ ወይም ፡ በዚያው ፡
ቄስ ፡ ዲያቆን ፡ ሊሆን ፡ ፈልጎ ፡ ወደሌላ ፡ አገር ፡
ቢደርስ ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ አብሮት ፡ የመጣ ፡ ይህ
ም ፡ ባይሆን ፡ የአገሩ ፡ ጳጳስና ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡
የጻፉለት ፡ ካልሆነ ፡ ሊሾም ፡ አይገባም ። በራሱ ፡
ፈቃድ ፡ ይህን ፡ ቢያደርግ ፡ የሾማቸው ፡ ሰዎች ፡
ክህነታቸው ፡ ይቅር ። እርሱም ፡ ከክህነቱ ፡
ይሻር ።

፻፶፮ አሥራ ፡ ስድስተኛ ። በስ ፡ ፴፰ ። ኤጲስቆጶስ ፡
እንዱን ፡ ካህን ፡ ቢለየው ፡ ሥራውንም ፡ እያ
ወቀ ፡ ሌላው ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ቢቀበለው ፡ ኤጲስ
ቆጶሱ ፡ ይሻር ። ካህናቱ ፡ ሥራው ፡ የቀናውን ፡
ኤጲስቆጶሱ በለዩት ፡ በርሱም ፡ ፈንታ ፡ ሌላ ፡

ተር ፡ እምኤጲስቆጶስናሁ ።

፻፶፯ ኒቅያ ፡ ዘ፵ወ፩ዱ ፡ ኢይደልዎ ፡ ለ፩ሂ ፡ እምኤጲስቆጶሳት ፡ ፈቲሐ ፡ ወአሢር ፡ እምነ ፡ ዘአውገዞ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ካልእ ፡ በጽድቅ ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ ሕያወ ፡ ዝኩ ፡ ዘአሠሮ ። ወእመሰ ፡ ሞተ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ለዘተሠይመ ፡ እምድኅሬሁ ፡ ብዉሕ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይፍትሖ ፡ ወሊቀ ፡ ጳጳሳትስ ፡ ከመ ፡ ይፍታሕ ፡ ወይአስር ፡ ሳዕለ ፡ ፪ኤሆሙ ፡ መባሕት ፡ ሎቱ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ በአምሳለ ፡ እግዚአ ፡ ቤት ።

፻፶፰ ዓሥር ፡ ወሳብዕ ፡ ረስጠብ ፡ ፳ቱ ፡ ረስጠጅ ፡ ፮ቱ ፡ እመቦ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘይትጌበር ፡ በምንትኒ ፡ እምግብረ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ይትመተር ።

፻፶፱ ረስጠጅ ፡ ዘ፷ወ፯ቱ ፡ ወኢይደልዎ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ከመ ፡ ያውድቅ ፡ ርእሶ ፡ እምሐራተ ፡ ክርስቶስ፡ ወይሠየም ፡ በምንትኒ ፡ እምግብራተ፡ ንጉሥ ፡ ወለእመ ፡ አጥብዐ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ይትፈለጥ ፡ እመዓርጊሁ ። እስመ ፡ እግዚእነ ፡ ይቤ ፡ "ኢይክል ፡ ፩ዱ ፡ ገብር ፡ ከመ ፡ ይትቀነይ ፡ ለ፪ኤ ፡ አጋእዝት ፡ ወእመ ፡ አኮሰ ፡ ያምዕዖ ፡ ለአሐዱ ፡ ወያሠምሮ ፡ ለካልኡ ።

፻፷ ዓሥር ፡ ወሳምን ፡ ጳክ ፡ ዘ፲ወ፩ዱ ፡ እመቦ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አው ፡ ፩ዱ ፡ እምላእካነ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘየሐውር ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ እንበለ ፡ የአዝዞ ፡ ዘይሠይሞ ፡ በቃሉ ፡ ወበከታቡ ፡ ይስደድ ፡ እመዓርጊ ፡ ሢመቱ ፡ ወእምተደምሮ ፡ ምእመናን ፡ ወእምክብሩ ፡ ዘነበረ ፡ ውስቴታ ።

፻፷፩ ዓሥር ፡ ወታስዕ ፡ ረስጠብ ፡ ፲ወ፰ቱ ፡ ኮሉ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አው ፡ ቀሲስ ፡ አው ፡ ዲያቆን ፡ እለ ፡ ይዘብጡ ፡ እምእመናን ፡ አው ፡ ዘኢኮነ ፡ ምእመነ ፡ ሶበ ፡ አበሱ ፡ እንዘ ፡ ይፈቅዱ ፡ በዝንቱ ፡ ከመ ፡ ይፍርሀዎሙ ፡ ሰብእ ፡ ይትመተሩ ።

፻፷፪ ፳ ፡ ዘጴጥሮስ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ወይትፈለጥ ፡ እምሢመቱ ፡ አመ ፡ ኮነ ፡ ተአማኔ ፡ በሐሳበ ፡ ኮከብ ፡ ወዘየአምን ፡ ነገረ ፡ ጠንቋልያን ፡ ወመሠርያን ፡ ወይትዌከፍ ፡ ቃሎሙ ።

፻፷፫ ፳ወ፩ዱ ፡ ረስጠጅ ፡ ፵ወ፱ቱ ፡ እመቦ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አው ፡ ቀሲስ ፡ አው ፡ ዲያቆን ፡ ዘተወከፉ ፡ ጥምቀተ ፡ ሐራ ፡ ጥቃ ፡ አው ፡ ቀረቡ ፡ ቍርባኖሙ ፡ ይትመተሩ ። ዘ፵ወ፫ቱ ፡ አው ፡ ጸለዩ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ይትፈለጡ ።

ቢሾሙ ፡ ከኤጲስቆጶስነቱ ፡ ይሻር ።

፻፶፯ ኒቅያ ፡ ፵፩ ። ሌላው ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ሳለ ፡ በእውነት ፡ ያወገዘውን ፡ ከኤጲስቆጳሳት ፡ ወገን ፡ አንዱስ ፡ እንኳ ፡ መፍታት ፡ ማሰር ፡ አይገባውም ። ኤጲስቆጶሱ ፡ ቢሞት ፡ ግን ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ የተሾመው ፡ ሊፈታው ፡ ይገባል ። ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ግን ፡ ሁለቱም ፡ ያወገዙትን ፡ ያስርም ፡ ይፈታም ፡ ዘንድ ፡ ሥልልጣን ፡ አለው ። እርሱ ፡ በቤት ፡ ጌታ ፡ አምሳል ፡ ነውና ።

፻፶፰ አሥራ ፡ ሰባተኛ ። ረስጠብ ፡ ፳ ። ረስጠጅ ፡ ፮ ። ከዓለማዊ ፡ ሥራ ፡ እንዳቸውን ፡ የሚሠራ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ቢኖር ፡ ይሻር ።

፻፶፱ ረስጠጅ ፡ ፷፯ ። ኤጲስቆጶስ ፡ ራሱን ፡ ከክርስቶስ ፡ አገልጋይነት ፡ አውጥቶ ፡ ለንጉሥ ፡ ከሚሠሩ ፡ ሥራዎች ፡ በማናቸውም ፡ ስፍራ ፡ መሾም ፡ አይገባውም ። በዚህ ፡ ጸንቶ ፡ ቢኖር ፡ ከሹመቱ ፡ ይሻር ። ጌታችን ፡ አንድ ፡ ባርያ ፡ ለሁለት ፡ ጌታ ፡ መገዛት ፡ አይቻለውም ፡ አለዚያ ፡ ግን ፡ አንዱን ፡ ያሳዝነዋል ፡ ሌላውንም ፡ ደስ ፡ ያሰኘዋል ፡ ብሏልና ። (ማቴ ፡ ፮ ፡ ፳፬) ።

፻፷ አሥራ ፡ ስምንተኛ ። ጳክ ፡ ፲፩ ። ኤጲስቆጶስ ፡ ወይም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ከሚያገለግሉ ፡ አንዱ ፡ የሾመው ፡ በቃሉ ፡ በደብዳቤው ፡ ሳያዘው ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ የሚሄድ ፡ ቢኖር ፡ ከሹመቱ ፡ መዓርግ ፡ ከምእመናንም ፡ ከመገናኘት ፡ ይለይ ። ጥንት ፡ ካለው ፡ ክብሩ ፡ ሁሉ ፡ ያለይ ።

፻፷፩ አሥራ ፡ ዘጠኝኛ ። ረስጠብ ፡ ፲፰ ። ኤጲስቆጶስ ፡ ሁሉ ፡ ወይም ፡ ቄስ ፡ ወይም ፡ ዲያቆን ፡ ከምእመናን ፡ ወገን ፡ የሆኑትንና ፡ ያልሆኑትን ፡ ሰዎች ፡ የሚማቱ ፡ በመማታታቸው ፡ ሰው ፡ እንዲፈራቸው ፡ ፈልገው ፡ በበደሉ ፡ ጊዜ ፡ ይሻሩ ።

፻፷፪ ፳ኛ ፡ ጴጥሮስ ፡ ፲፪ ። ኮከብ ፡ ቈጣሪ ፡ የሆነ ፡ የጠንቋዮችንና ፡ የሥራይ ፡ አድራጊዎችን ፡ ነገር ፡ የሚያምን ፡ ቃላቸውንም ፡ የሚቀበል ፡ ከሹመቱ ፡ ይሻር ።

፻፷፫ ፳፩ኛ ። ረስጠጅ ፡ ፵፱ ። የሐራ ፡ ጥቃን ፡ ጥምቀት ፡ የተቀበሉ ፡ ወይም ፡ ቍርባናቸውን ፡ የቈረቡ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወይም ፡ ቄስ ፡ ወይም ፡ ዲያቆን ፡ ቢኖሩ ፡ ይሻሩ ። ፵፫ ፡ ረስጠጅ ። ወይም ፡ አብረዋቸው ፡ ቢጸልዩ ፡ ይለዩ ።

፪፻፬ ፳ወ፪ቱ ፡ ዘዕንቈራ ፡ ፲ወ፯ቱ ፡ ወኵሉ ፡ ዘተሠይመ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በሀገሩ ፡ ወኢተወክፍዎ ፡ ሰብአ ፡ ዚአሃ ፡ አው ፡ ዘይበዝኁ ፡ ጉባኤ ፡ ወኮነ ፡ በኵሉ ፡ ግብሩ ፡ ተጋእዞ ፡ ወለእመ ፡ ፈቀዱ ፡ ከመ ፡ ይሑሩ ፡ ኀበ ፡ ካልእ ፡ መንበር ፡ ወይትበእስዎ ፡ ለዘተሠይመ ፡ ዲቤሃ ፡ ቅድመ ፡ ለይትሌለይ ። ወለእመ ፡ ተትሕተ ፡ ወአፍቀረ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ቀሲስ ፡ ዘኮነ ፡ ባቲ ፡ ቅድመ ፡ ይኩን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ይኩን ፡ ወይትዓወቅ ፡ ሎቱ ፡ ክብረ ፡ ኤጲስቆጶስናሁ ፡ ዘኮነ ፡ ባቲ ፡ ወይዕበይ ፡ በውስተ ፡ መንበር ፡ ባሕቲቱ ። ወለእመ ፡ አስተናሥአ ፡ ጋእዘ ፡ ላዕለ ፡ ውእቱ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘውስቴ ፡ ውእቱ ፡ ብሔር ፡ ወላዕለ ፡ ዘሚጦ ፡ ይሥዐር ፡ ካዕበ ፡ እምሢመተ ፡ ቅስና ። ወለእመሰ ፡ ውእቱ ፡ አስተሐመመ ፡ ላዕለ ፡ ዛቲ ፡ ኤጲስቆጶስና ፡ እንተ ፡ ኮነ ፡ በይእቲ ፡ ሀገር ፡ እምድኅረ ፡ ሠነየ ፡ ይኩን ፡ ወይኅድግ ፡ መዓርገ ፡ ቅስናሁ ፡ ካዕበ ።

፪፻፭ ፳ወ፫ቱ ፡ ረስጠጅ ፡ ፷ወ፬ቱ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ሶበ ፡ አስተዋደይዎ ፡ ምእመናን ፡ ንጹሓን ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይጸውዕዎ ፡ ኤጲስቆጶሳት ። ወሶበ ፡ መጽአ ፡ ወተአመነ ፡ በአበሳሁ ፡ ይገሥፅዎ ፡ ላዕለ ፡ ዘገብረ ፡ ወይኰንንዎ ። ወለእመ ፡ አበየ ፡ መጺአ ፡ ይፌንዉ ፡ ኀቤሁ ፡ ካዕበ ፡ እምኤጲስቆጶሳት ፡ ምዕረ ፡ ወካዕበ ፡ ወለእመ ፡ አበየ ፡ መጺአ ፡ ይፌንዉ ፡ ካዕበ ፡ ሣልሳየ ፡ ወለእመ ፡ ኢመጽአ ፡ የአገዝዙ ፡ ኀቤሁ ፡ ጉባኤ ፡ መኳንንት ፡ ከመ ፡ ኢየሐሊ ፡ ኢመጺኦቶ ፡ ኀበ ፡ ጉባኤ ፡ ሠናየ ፡ ይኰንንዎ ።

፪፻፮ ፳ወ፬ቱ ፡ ኒቅያ ፡ ወለእመ ፡ ነገዱ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ እመናብርቲሆሙ ፡ ኢየንኑ ፡ ተመይጦ ፡ እም፰ቱ ፡ አውራኅ ፡ ወለእመ ፡ አፈድፈዱ ፡ እምዝንቱ ፡ እንበለ ፡ ዓጸባ ፡ ወእንበለ ፡ ትእዛዘ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አው ፡ አብዛሉ ፡ በዓለ ፡ ትንሣኤ ፡ በውስተ ፡ ካልእ ፡ እንበለ ፡ መናብርቲሆሙ ፡ ይሰደዱ ፡ እምሢመተ ፡ ክህነት ።

፪፻፯ ፳ወ፭ቱ ፡ ረስጠጅ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ እመቦ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘተወክፎ ፡ ለካህን ፡ ዘፈለሰ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘዚአሁ ፡ በአምሳለ ፡ ፩ዱ ፡ አምን ፡ ካህናት ፡ ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ ኀሠሦ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘዚአሁ ፡ ወኢተመይጠ ፡ ይስደድ ።

፪፻፰ ረስጠጅ ፡ ፳ወ፮ቱ ፡ ወዘወሀበ ፡ ንዋየ ፡ ለኤ



፪፻፬ ፳፪ኛ ። ዕንቈራ ፡ ፲፯ ። በአገሩ ፡ ኤጲስቆጶስነትን ፡ የተቀበለ ፡ ሁሉ ፡ የአገሩም ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ የበዙት ፡ ጉባኤ ፡ ባይቀበሉት ፡ በሥራውም ፡ ሁሉ ፡ ጠብ ክርክር ፡ ቢሆን ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ሀገረ ፡ ስብከት ፡ ሊሄድ ፡ ቢወድ ፡ በእርስዋ ፡ ላይ ፡ አስቀድሞ ፡ የተሾመውን ፡ ቢጣሉት ፡ ይለይ ። ቢዋረድ ፡ ኤጲስቆጶስነት ፡ ሳይሾም ፡ በነበረበትም ፡ መዓርግ ፡ ቄስ ፡ ሊሆን ፡ ቢወድ ፡ ተሹሞባት ፡ የነበረችው ፡ የኤጲስቆጶስነቱ ፡ መዓርግ ፡ ይታወቅለት ። በመንበር ፡ ብቻ ፡ ከፍ ፡ ይበል ። በዚያ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ ኤጲስቆጶስነት ፡ በሾመውም ፡ ላይ ፡ ጠብ ፡ ክርክር ፡ ቢያነሣ ፡ ዳግመኛ ፡ ከቅስናው ፡ መዓርግ ፡ ይሻር ። በዚያች ፡ አገር ፡ ተሹሞ ፡ ስነበረባት ፡ ኤጲስቆጶስነት ፡ ቢያስብ ፡ ግብሩ ፡ ከአማረ ፡ የቅስናውን ፡ መዓርግ ፡ ትቶ ፡ ዳግመኛ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ይሁን ።

፪፻፭ ፳፫ኛ ። ረስጠጅ ፡ ፷፬ ። ኤጲስቆጶስን ፡ ንጹሓን ፡ ምእመናን ፡ ቢከሱት ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ሊጠሩት ፡ ይገባል ። መጥቶ ፡ በደሉን ፡ ቢያምን ፡ በሠራው ፡ ሥራ ፡ ይቅጡት ፡ ይፍረዱበትም ። አልመጣም ፡ ቢል ፡ ከኤጲስቆጶሳት ፡ ወገን ፡ መልእክተኛ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ይላኩበት ። አሁንም ፡ አልመጣም ፡ ቢል ፡ ሦስተኛ ፡ ጊዜ ፡ ይላኩበት ። ባይመጣም ፡ የተሰበሰቡት ፡ ሸረንጎል ፡ ብለው ፡ ይዘዙ ። ወደ ፡ ጉባኤው ፡ አለመሄድ ፡ መልካም ፡ ሆነልኝ ፡ ብሎ ፡ እንዳያስብ ።

፪፻፮ ፳፬ኛ ። ኒቅያ ። ኤጲስቆጶሳት ፡ ከሀገረ ፡ ስብከታቸው ፡ ወደሌላ ፡ አገር ፡ ቢሄዱ ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ የበለጠ ፡ አይኑሩ ። ችግር ፡ ሳይገጥማቸው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱም ፡ ሳይፈቅድላቸው ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ቢኖሩ ፡ ወይም ፡ ሀገረ ፡ ስብከታቸውን ፡ ትተው ፡ በሌላ ፡ አገር ፡ በዓለ ፡ ትንሣኤን ፡ ቢያከብሩ ፡ ከሹመታቸው ፡ ይሻሩ ።

፪፻፯ ፳፭ኛ ። ረስጠጅ ፡ ፲፪ ። የሚያገለግለውን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትቶ ፡ የመጣውን ፡ ካህን ፡ ከካህናት ፡ ወገን ፡ በአንዱ ፡ አምሳል ፡ የተቀበለው ፡ ኤጲስቆጶስ ቢኖር ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የአገሩ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ቢፈልገውና ፡ ባይመለስ ፡ ይለይ ።

፪፻፰ ረስጠጅ ፡ ፳፮ ። ገንዘብ ፡ ሰጥቶ ፡ የተሾመ ፡

ጺስቆጶስና ፡ ወሢመቱሂ ፡ ትኩን ፡ ከመ ፡ ወኢ ምንት ፡ ወወሃቢሃ ፡ ይትኰነን ። ወዝንቱኒ ፡ ውፁእ ፡ እምዘነበረ ፡ ውስቴቱ ፡ በአንቀጸ ፡ ካህ ናት ፡ ወበዘተርፈ ፡ አንቀጽ ።



ኤጲስቆጶስ ፡ ሹመቱ ፡ ኢምንት ፡ (የተናቀች) ፡ ትሁን ። ሿሚዋም ፡ ይቀጣ ፡ ይኸውም ፡ በካህ ናት ፡ አንቀጽ ፡ ተጨምሮ ፡ ከተነገረውና ፡ በቀረውም ፡ አንቀጽ ፡ ከሚገኘው ፡ የተውጣጣ ፡ ነው ። (ፍ ፡ ነ ፡ ፪፻፳፭ ፡ ፫፻፲፮) ።

## አንቀጽ ፡ ሳድስ ፡

### በእንተ ፡ ቀሳውስት ።

፪፻፱ ወዘይደሉ ፡ ውስቴቱ ፡ ይትከፈል ፡ ኀበ ፡ ፮ቱ ፡ አክፋል ፡ ዘትእዛዛት ፡ ርቱዓት ፡ ወሢመታት ፡ ወመዓርጋት ፡ ወሕገጋት ፡ ወምክንያተ ፡ መቲር ወዘኢይከልእ ፡ እምነ ፡ ተልእኮ ።

፪፻፲ ቀዳሚ ፡ በእንተ ፡ ትእዛዛት ፡ ርቱዓት ፡ ይቤሎ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ለቲቶ ፡ ረድኡ ፡ ዘ፲ወ፩ዱ ፡ አእምር ፡ በዘኀደገከ ፡ ከመ ፡ ታስተራትዕ ፡ ግብረ ፡ ዘተርፈ ፡ ወትሢም ፡ ቀሳውስተ ፡ በበ ሀገሩ ፡ በከመ አዘዝኩከ ፡ ዘአልቦቱ ነውር ፡ ላዕሌሁ ፡ ወዘአሐተ ፡ ብእሲተ አውሰበ ፡ ወዘ ሎቱ ፡ ውሉድ ፡ ምእመናን ፡ ዘኢያስተዋድይ ዎሙ ፡ በምርዓት ፡ እስ ፡ ኢኮኑ ፡ ዝሉፋነ ፡ ወእለ ፡ ይትኤዘዙ ። እስመ ፡ ቀሲስ ፡ ርቱዕ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ዘአልቦቱ ፡ ሐሜት ፡ አምሳለ ፡ መጋቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢይኩን ፡ ዘየሐ ውር ፡ በምክረ ፡ ነፍሱ ፡ ወኢተቀያሚ ፡ ወኢ ዘያበዝኅ ፡ ሰትየ ፡ ወይን ፡ ወኢይኩን ፡ ዘያፈ ጥን ፡ እዴሁ ፡ ለዘቢጥ ፡ ወኢይኩን ፡ መፍቀሬ ፡ ረባኅ ፡ ርኩስ ። አላ ፡ ይኩን ፡ መፍቀሬ ፡ እን ግዳ ፡ ወመፍቀሬ ፡ ሠናያት ፡ ንጹሐ ፡ ወጻድቀ ፡ ወኄረ ፡ ወእኃዜ ፡ ነፍሱ ፡ እምነ ፡ ፍትወታት ፡ ወተራዳኢ ፡ ለትምህርተ ፡ ነገረ ፡ ሃይማኖት ፡ ወዘይክል ፡ ናዝዞተ ፡ በትምህርተ ፡ ጽድቅ ፡ ወይ ዛስፎሙ ፡ ለእለ ፡ ይትከሐዱ ፡ ወይትሜየኑ ።

፪፻፲፩ ቀጠጅ ፡ ፲ወ፩ ፡ ኢይሠየም ፡ ቀሲስ ፡ ዘእንበለ ፡ በ፴ ፡ ዓመት ፡ እመኒ ፡ ኮነ ፡ ድልወ ፡ አላ ፡ ይት ዐገሥ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ዝንቱ ፡ መዋዕል ። እስመ ፡ እግዚእነሂ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡

## አንቀጽ ፡ ፮ ።

### ስለ ፡ ቀሳውስት ።

፪፻፱ በዚህ ፡ ውስጥ ፡ ሊያደርጉት ፡ የሚገባው ፡ ነገር፡ ከስድስት ፡ ይከፈላል ። እነርሱም ፡ የቀኑ ፡ ትእ ዛዛት ፡ ሹመታት ፡ መዓርጋት ፡ ሕጋጋት ፡ የመ ሻር ፡ ምክንያትና ፡ ከአገልግሎት ፡ የማይከለ ክል ፡ ምክንያት ፡ ናቸው ።

፪፻፲ መጀመሪያው ፡ ስለ ፡ ቀኑት ፡ ትእዛዛት ፡ ይናገ ራል ። ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ ለደቀ ፡ መዝሙሩ ለቲቶ ፡ እንዲህ ፡ አለው ። ፲፩ ። ከእኔ ፡ የቀረ ውን ፡ ሥራ ፡ ታከናውን ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ተው ሁህ ፡ እወቅ ፡ ነውር ፡ የሌለባቸውን ፡ ቀሳው ስት ፡ በያገሩ ፡ ትሾም ፡ ዘንድ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ያገባውን ፡ በመዳራት ፡ የማይከሰሶ ውና ፡ የተንቀፉ ፡ ያይደሉ ፡ ታዛዦች ፡ የሆኑ ፡ ደጋግ ፡ ልጆች ፡ ያሉትን ፡ ትሾም ፡ ዘንድ ። ቄስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሹም ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ ነውር ፡ የሌለበት ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ይገባዋ ልና ። በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ የሚኖር ፡ አይሁን ። ቂመኛ ፡ አብዝቶ ፡ የሚጠጣ ፡ ለመማታት ፡ እጁን ፡ የሚያፈጥን ፡ አይሁን ። ያልታዘዘ ፡ ትርፍን ፡ የሚወድ ፡ አይሁን ። እንግዳ ፡ መቀ በልን ፡ የሚወድ ፡ በጎ ፡ ሥራን ፡ የሚወድ ፡ ንጹሕ ፡ ጻድቅ ፡ ቸር ፡ የሆነ ፡ ከፍትወታት ፡ ሰውነቱን ፡ ወስኖ ፡ ገቶ ፡ የያዘ ፡ የሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ ነገርን ፡ በማስተማር ፡ የሚረዳ ፡ የእውነት ፡ ትምህርትን ፡ በማስተማር ፡ ማረጋ ጋት ፡ የሚችል ። የሚክዱትንና ፡ የሚተናኰሉ ትን ፡ የሚከራከራቸው ፡ ይሁን ፡ እንጂ ። (ቲቶ ፡ ፩ ፡ ፭-፲፩) ።

፪፻፲፩ ቀጠጅ ፡ ፲፩ ። ቄስ ፡ በሠላሳ ፡ ዓመቱ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አይሾም ። ምንም ፡ የበቃ ፡ ቢሆን ፡ ይህ፡ ዘመን ፡ እስኪሞላው ፡ ድረስ ፡ ይቆይ ፡ እንጂ ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በ፴ ፡ ዘመኑ ፡

ተጠምቀ ፡ በ፴ ፡ ዓመት ፡ ወእምዝ ፡ እንዘ ፡ ይምህር ።

፪፻፲፪ በስ ፡ ፹ወ፱ቱ ፡ ወኢያኩን ፡ ፩ዱሂ ፡ ቀሲስ ፡ ዘኢየእምር ፡ ነገረ ፡ መጻሕፍት ፡ አምላካውያት፡ ሠናያት ፡ ወፈድፋደሰ ፡ አርባዕተ ፡ ወንጌላተ ። ዘ፹ወ፺ቱ ወኢይኩን ፩ዱሂ ፡ ቀሲስ ዘኢተን እደ ፡ በስምዐ ፡ ሐምስቱ ፡ እደው ።

፪፻፲፫ ዳግም ፡ ክፍል ፡ በእንተ ፡ ሢመቱ ። ረስጣ ፡ ፳ወ፪ቱ ፡ ፶ወ፩ቱ ፡ ወለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ኤጲስቆ ጶስ ፡ ከመ ፡ ይሢም ፡ ቀሲስ ፡ ያንብር ፡ እዴሁ ፡ ላዕለ ፡ ርእሱ ፡ ወቀሳውስትኒ ፡ ኵሎሙ ፡ ይግ ሥሥዎ ፡ ቀዊሞሙ ፡ ወይጸልዩ ፡ ላዕሌሁ ፡ በእ ምሳለ ፡ ዘብህልነ ፡ በእንተ ፡ ኤጲስቆጶስ ። በስ ፡ ፲ቱ ፡ ወኢይሠየም ፡ ቀሲስ ፡ ወዲያቆን ፡ ዘእን በለ ፡ በምክረ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘውእቶሙ ፡ ታሕ ተ ፡ ሥልጣኑ ። ረስጠጅ ፡ ፪ቱ ፡ ወይሢም ፡ ኤጲ ስቆጶስ ፡ ባሕቲቱ ፡ እስመ ፡ ሣልሳይ ፡ መዓርጊሁ፡

፪፻፲፬ ሣልስ ፡ ክፍል ፡ በእንተ ፡ ሥርዓት ፡ ድስቅ ፡ ፩ዱ ፡ እስመ ፡ ቀሲስ ፡ በእምሳለ ፡ መምህር ። ዘ፯ቱ ፡ ወይኩኑ ፡ ቀሳውስት ፡ በኀቤክሙ ፡ መምህራነ ፡ ለእእምሮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወተ ወክፉ ፡ እምኔሆሙ ፡ ነገረ ፡ ሃይማኖት ፡ ርት ዕት ፡ ወትምህርተ ፡ ጥይቅተ ፡ እምዘመሀርና ክሙ ፡ እመንገሌነ ። ወከመዝ ፡ እዘዘነ ፡ እግዚ እነ ፡ ሶበ ፡ ፈቀደ ፡ ይፈንወነ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ "ሑሩ ፡ ወመሀሩ ፡ ኵሎ ፡ እሕዛበ ፡ ወእጥም ቅዎሙ ፡ በስመ ፡ እብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወመሀርዎሙ ፡ ይዕቀቡ ፡ ኵሎ ፡ ዘአዘ ዝኩክሙ" ።

፪፻፲፭ ዘ፴ወ፬ቱ ፡ ወለቀሲስ ፡ ሎቱ ፡ ፩ዱ ፡ ሥልጣን ፡ ለባሕቲቱ ። ወውእቱ ፡ ከመ ፡ ይምሀር ፡ ወያ ጥምቅ ፡ ወይቀድስ ፡ ወይባርክ ፡ ሕዝበ ። ዘ፳ቱ ፡ ወየሀሉ ፡ ምስለ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ውስተ ፡ መን በረ ፡ ፍትሕ ። ረስጣ ፡ ፶ወ፳ቱ ፡ ወይባርክ ፡ ወኢይትባረክ ፡ እምዘውእቱ ፡ ይንእስ ፡ ወይ ትመጠው ፡ እውሎግያ ፡ እምኤጲስቆጶስ ፡ ወእ ምሱታፌሁ ፡ ቀሲስ ፡ ወያንብር ፡ እዴሁ ፡ ላዕለ ፡ እርእስተ ፡ ሕዝብ ። ወኢይሢም ፡ ፩ደሂ ፡ ወኢይምትሮ ፡ ወኢያውፅእ ፡ ለዘውስቴቱ ፡ ሕጸጽ ። ቃል ፡ ዘውስተ ፡ መጽሐፈ ፡ ቀኖናተ ፡ ሐዋርያት ። ወያውፅእ ፡ ለዘውእቱ ፡ ሕጹጽ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘቦ ፡ ዘይደልዎ ፡ ሥቃይ ።



ተጠምቆ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ማስተማርን ፡ ጀም ሮአልና ።

፪፻፲፪ በስ ፡ ፹፱ ። መልካም ፡ የሆኑትን ፡ የእምላክን ፡ መጻሕፍት ፡ ነገር ፡ ይልቁንም ፡ አራቱን ፡ ወንጌል ፡ ያላወቀ ፡ አንዱ ፡ ስንኳ ፡ ቄስ ፡ አይሁን፡ ፹፺ ፡ በስ ። እምስት ፡ ሰዎች ፡ ያልመሰከሩለት ፡ አንዱ ፡ ስንኳ ፡ ቄስ ፡ አይሁን ።

፪፻፲፫ ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ስለ ፡ ሹመቱ ፡ ይናገራል ። ረስጣ ፡ ፳፪ ፡ ፶፩ ። ኤጲስቆጶስ ፡ ቄስን ፡ ይሾም ፡ ዘንድ፡ቢወድ፡በእንብሮተ፡እድ፡ይሹመው።ቀሳ ውስትም ፡ ሁሉ ፡ ቆመው ፡ ይዳሱት ። ስለ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በተናገርነውም ፡ እምሳል ፡ ይጸ ልዩለት ። (ፍት ፡ ነገ ፡ ፭ ፡ ፻፲) ። በስ ፡ ፲ ። ያለ ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ ፈቃድ ፡ ቄስም ፡ ዲያቆንም ፡ አይ ሾም ። እነርሱም ፡ ከሥልጣኑ ፡ በታች ፡ ናቸው ። ረስጠጅ ፡ ፪ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ መዓርጉ ፡ ሦስተኛ ፡ ነውና ፡ ብቻውን ፡ ይሹም ።

፪፻፲፬ ሦስተኛው ፡ ክፍል ፡ ስለ ፡ ሥርዓት ፡ ይናገራል። ድስቅ ፡ ፩ ። ቄስ ፡ እኮ ፡ የመምህር ፡ እምሳል ፡ ነው ። ፯ ፡ ድስቅ ። እግዚአብሔርን ፡ ለማሳ ወቅ ፡ ቀሳውስት ፡ በናንተ ፡ ዘንድ ፡ መምህራን ፡ ይሁኑ ። የቀናች ፡ የሃይማኖትን ፡ ነገር ፡ ከእነ ርሱ ፡ ተቀበሉ ። ካስተማርናችሁም ፡ ወገን ፡ የተረዳች ፡ ትምህርትንም ፡ ተቀበሉ ። ጌታ ችን ፡ ሊልከን ፡ በወደደ ፡ ጊዜ ፡ ሂዳችሁ ፡ እሕዛብን ፡ ሁሉ ፡ አስተምሩ ፡ በእብና ፡ በወ ልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ስም ፡ አጥምቋ ቸው ፡ ያዘዝኋችሁን ፡ ሁሉ ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ አስተምሩዋቸው ፡ ብሎ ፡ እንደዚሁ ፡ እዘዘን ። (ማቴ ፡ ፳፰ ፡ ፲፱ - ፳) ።

፪፻፲፭ ፴፬ ፡ ድስቅ ። ለቄስ ፡ እንድ ፡ ሥልጣን ፡ ብቻ ፡ እለው ። ይኸውም ፡ ያስተምር ፡ ዘንድ ፡ ያጠም ቅ ፡ ዘንድ ፡ ይቀድስ ፡ ዘንድ ፡ ይባርክ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ፳ ፡ ድስቅ ። በፍርድም ፡ ወንበር ፡ ከኤጲ ስቆጶሱ ፡ ጋር ፡ ይቀመጥ ። ረስጣ ፡ ፶፳ ። ይባርክ እንጂ ፡ ከእርሱ ፡ ከሚያንሰው ፡ አይባረክ ። ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ከኤጲስቆጶሱ ፡ ይቀበል ። ከንደኛውም ፡ ከቄሱ ፡ ይቀበል ። በሕዝብ ፡ ራስ ላይ ፡ እጁን ፡ ያስቀምጥ ። አንዱን ፡ ስንኳ ፡ አይሹም ፡ አይሻረውም ። ጉድለት ፡ የተገኘበ ትንም ፡ አያውጣው ። በሐዋርያት ፡ የሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ቃል ፡ ለመሻር ፡ የሚ ያበቃ ፡ ነውር ፡ ከተገኘበት ፡ ግን ፡ ያስወጣው ።

፪፻፲፮ ራብዕ ፡ ክፍል ፡ በእንተ ፡ ትእዛዝ ፡ ዘይኤዝዝዎ፡ ሎቱ ፡ ይቤ ፡ ጴጥሮስ ፡ በውስተ ፡ መልእክቱ ፡ ቀዳማዊ ፡ ወለቀሲሳን ፡ ዘኀቤክሙ ፡ አስተበቍዖሙ ፡ አነ ፡ ቀሲስ ፡ ካልአሙ ፡ እንዘ ፡ እብል ረዐዩ ፡ መርዔቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘሀለዉ ፡ ኀቤክሙ ። ወሐውጽዎሙ ፡ በሕዋጼ ፡ እግዚአብሔራዊት ፡ አኮ ፡ በኀይል ፡ ዳእሙ ፡ በፈቃድ ፡ ወኢበመንፈስ ፡ እኩይ ፡ አላ ፡ በልብ ፡ ሰላማዊ ፡ ወአኮ ፡ ከመ ፡ ኢጋእዝት ፡ ዘይፈርህ ፡ አላ ፡ ኩኑ ፡ በአምሳለ ፡ መርዓት ፡ ለኖላዊ ፡ ከመ ፡ አመ ፡ አስተርአየ ፡ ሊቀ ፡ ኖሎት ፡ ትንሥኡ ፡ እምኔሁ ፡ አክሊለ ፡ ስብሐት ፡ ዘኢይጸመሂ ።

፪፻፲፯ ረስጠብ ፡ ፲ወ፫ቱ ፡ ወይደልዎሙ ፡ ለቀሳውስት፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ በአምሳለ ፡ ሊቃናት ፡ በኀሁ ፡ ኀለፉ ፡ እምወሰነ ፡ አሐቲ ፡ ብእሲት ፡ ከመ ፡ ይሳተፉ ፡ ምሥጢራተ ፡ ምስለ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወይትራድእዎ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ በምንትኒ ፡ ወይትጋብኡ ፡ በፍቅር ፡ ኀበ ፡ ኖላዊሆሙ ።

፪፻፲፰ ይቤ ፡ መተርጕም ፡ ሊተሰ ፡ ይመስለኒ ፡ ከመ ፡ ልሂቃን ፡ ዘይቤ ፡ ፳ወ፬ቱ ፡ ቀሳውስት ፡ መላእክት ፡ መንፈሳውያን ። ወቀሳውስትኒ ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ የማን ፡ ያስተሐምሙ ፡ ሰረድኤት ፡ በውስተ ፡ ምሥዋዕ ። ከመ ፡ ያክብርዎ ፡ ለዘይደልዎ ፡ ክብር ፡ ወይመንንዎ ፡ ለዘይደልዎ ፡ ምናኔ ። ወቀሳውስትሰ ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ ፀጋም ፡ ያስተሐምሙ ፡ በእንተ ፡ ጉባኤ ፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ ህዱአነ ፡ ወኢያደንግፁ ፡ ግሡፃነ ፡ በኵሉ ፡ ተግሣፅ ፡ ወይትአዘዙ ፡ በኵሉ ፡ ተአዝዞ ።

፪፻፲፱ ዶቅ ፡ ዘ፬ወ፯ቱ ፡ ወኢይደሉ ፡ ለቀሳውስት ፡ ከመ ፡ ይሑሩ ፡ ቅድመ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በዓውደ ፡ ምሥዋዕ ፡ ወኢይባኡ ፡ ኀበ ፡ ምሥዋዕ ፡ ቅድሜሁ ፡ ወኢይንበሩ ፡ ዓውደ ፡ መንበር ፡ ዘእንበለ ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ማእከሌሆሙ አላ ፡ ይባኡ ፡ በድኅሬሁ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ወኢይንበሩ ፡ ዓውደ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘኢኮኑ ፡ ድዉያነ ፡ አው ፡ ዘነገዱ ፡ ወይኩን ፡ ዝንቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ሎሙ ።

፪፻፳ መጅ ፡ ዘ፯ቱ ፡ ወኢይሑር ፡ ቀሲስ ፡ ኀበ ፡ ምሳሕ ፡ ውስተ ፡ ክብካብ ፡ ዘአውሰበ ፡ ፪ተ ፡ አንስተ ። እስመ ፡ ዘይነብር ፡ ምስለ ፡ ክልኤቱ ፡



፪፻፲፮ አራተኛው ፡ ክፍል ፡ ስለ ፡ ትእዛዝ ፡ የሚያዙትን ፡ ይናገራል ። ጴጥሮስ ፡ በመጀመሪያው ፡ መልእክቱ፥ እንዲህ ፡ አለ ። በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ያሉትን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወገን ፡ ምእመናንን ፡ ጠብቁ ፡ ብዬ ፡ ወንድማቸው ፡ እኔ ፡ ቄሱ ፡ እማልዳቸዋለሁ ። እግዚአብሔር ፡ ባዘዘው ፡ መጐብኘትም ፡ ጐብኟቸው ። በፈቃድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በግድ ፡ አይደለም ። ፍቅር ፡ በሌለውም ፡ ልቡና አይደለም ። ፍቅርን ፡ በያዘ ፡ ልቡና ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደሚያስፈራሩ ፡ ጌቶች ፡ አይደለም ። ለጠባቂያቸው ፡ እንደሚገዙ ፡ መንጋዎች ፡ ሁኑ፡ እንጂ ። የበጎች ፡ (የምእመናን) ፡ አለቃ ፡ በተገለጠ ፡ ጊዜ ፡ የማይጠወልግ ፡ የምስጋና ፡ አክሊልን ፡ ትቀዳጁ ፡ ዘንድ ። (፩ጴጥ ፡ ፭ ፡ ፬) ።

፪፻፲፯ ረስጠብ ፡ ፲፫ ። ቀሳውስት ፡ በአንዲት ፡ ሴት ፡ ተወስነው ፡ ባለፉ ፡ በሊቃናት ፡ አምሳል ፡ መሆን ፡ ይገባቸዋል ። ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ከኤጲስቆጶሱ ፡ ይቀበሉ ፡ ዘንድ ። በማናቸውም፥ ሁሉ ፡ ይረዱት ፡ ዘንድ ። በፍቅር ፡ ወደ ፡ ጠባቂያቸው ፡ ይሰበሰቡ ፡ ዘንድ ።

፪፻፲፰ ተርጓሚው ፡ እንዲህ ፡ አለ ። እኔ ፡ ግን ፡ ሊቃናት ፡ ያላቸው ፡ ሃ፬ቱን ፡ ካህናተ ፡ ሰማይ ፡ ይመስለኛል ። በቀኝ ፡ ያሉ ፡ ቀሳውስትም ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ ለመርዳት ፡ ያስቡ ። ክብር ፡ የሚገባውን ፡ ያከብሩት ፡ ዘንድ ፡ ከላይ ፡ መቆም ፡ የሚገባውን ፡ ከላይ ፡ ያደርጉት ፡ ዘንድ ፡ ከታች ፡ መቆም ፡ የሚገባውንም ፡ ከታች ፡ ያቆሙት ፡ ዘንድ ። በግራ ፡ ያሉ ፡ ቀሳውስት ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ጉባኤው ፡ ይትጉ ፡ ጸጥተኞች ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ። የተቀጡትንም ፡ አያስደንግጡ ፡ ፈጽመውም ፡ ይታዘዙ ።

፪፻፲፱ ዶቅ ፡ ፵፯ ። ቀሳውስት ፡ በመንበሩ ፡ ዙሪያ ፡ በኤጲስቆጶሱ ፡ ፊት ፡ መሄድ ፡ አይገባቸውም ። ከእርሱም ፡ አስቀድመው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ መግባት ፡ አይገባቸውም ። ከኤጲስቆጶሱ ፡ በኋላ ፡ ይግቡ ፡ እንጂ ። ሕመምተኞች ፡ ወይም ፡ መንገደኞች ፡ ካልሆኑ ፡ በቀር ፡ በአንጻሩ ፡ አይቀመጡ ። ይህ ፡ ሕግ ፡ ይጸናላቸው ።

፪፻፳ መጅ ፡ ፯ ። ሁለት ፡ አኅትማማቾችን ፡ ወደ ፡ አገባ ፡ ሰው ፡ ሠርግ ፡ ቄሱ ፡ ለምሳ ፡ አይሂድ ። ሁለት ፡ አኅትማማቾችን ፡ ያገባ ፡ ሰው ፡ ንስሐ ፡

አኃት : ዘይደልዎ : ንስሓ : እፎኬ : ይከውን : ቀሲስ : ምስሌሁ : ይብላዕ : አመብልዕ : ዘከመገ ።

፪፻፳፩ በስ : ፻ወ፩ዱ : ወኢይወስከ : ፩ዱሂ : እምቀሳውስት : ምንተኒ : ክበደ : ላዕለ : ሕዝብ : ውፁእ : እምቀኖና : አበዊነ : ሐዋርያት ። ሉቃስ : ወይእዜኒ : ለምንት : ታሜክርዎ : ለእግዚአብሔር : ወታፀውርዎሙ : አርዑተ : ዲበ : ክሳዶሙ : ለአርዳእ : ዘኢክህልነ : ንሕነ : ወኢአበዊነ : ከመ : ንፁር ። ወበእንተ : ዝንቱ : አነ : እሬትዕ : ከመ : ኢትወስኩ : ድካመ : ላዕለ : እለ : ተመይጡ : ኀበ : እግዚአብሔር ። ወናሁ : ሠምረ : መንፈስ : ቅዱስ : ወሠመርነ : ካዕበ : ንሕነኒ : ከመ : ኢናንብር : ላዕሌክሙ : ክበደ : ዘይበዝኅ : እምዝንቱ : ግብር : ወዘኢይደሉ : ትግበርዎ ።

፪፻፳፪ በስ : ፻ወ፪ቱ : ወኢይትዐረቅ : ቀሲስ : ግሙራ : ቅድመ : መኑሂ : እምስብእ : ዘእንበለ : በጊዜ : ዓጸባ ። ወእምከመ : ዐፀቦ : ወፈቀደ : ይሑር : ኀበ : ቤተ : ብእሲ : ይሑር : ምስለ : እለ : ከማሁ በመዓርግ : ባሕቲቶሙ : ቅድመ : ይትጋብኡ : ሕዝባውያን ።

፪፻፳፫ ዘኒቅያ : ፻ወ፫ቱ : ወይትጋብኡ : ቀሳውስት : ኀበ : ኤጲስቆጶሳቲሆሙ : ፪ተ : ጊዜያተ : በበ ዓመት : ወይርአዩ : በእንተ : ኵሉ : ዘይፈቅድዎ : ሎቱ ።

፪፻፳፬ ኃምስ : ክፍል : ዘይነግር : በእንተ : ምክንያት : እንተ : ታወድቆ : እመዓርጊሁ ። ወዛቲ : እምኔሃ : ዘተነግረ : ዝክረ : እንብሮታ : ወኍላቄሃ : በአንቀጸ : ኤጲስቆጶስ : ወኵለንታሁ : ዝውእቱ : ወይትመተር : ኵሉ : ቀሲስ : ዘይነሥእ : ሢመተ : ቅስና : በሕልያን : አው : በተገርሞ : አው : በአድልዎ : አው : በትምይንት : አው : በአስፍዎ : ሕልያን ። አው : ዘተሠይመ : ፪ተ : ጊዜያተ ። አው : ዘአውሰበ : ፪ተ : አንስተ : አው : ዘይትሀከይ : ምሂሮተ : ሕዝቡ ። አው : ዘይትኄየዮሙ : ለነዳያን : ካህናት ; ወኢይትራድኦሙ : አው : ዘኢይትዌከፍ : ንስሓሁ : ለኃጥእ : አው : ዘተሀውቀ : በስምዐ : ሐሰት : ወውዴተ : ሰብእ : አው : ዘይገብር : ትዕቢተ : አው : ዘየአምራ : ለሕግ : ወኢይገብር : ባቲ : አው : ዘየዘልፍ : ለካረ : ወገቢረ : እከይ : ወዘያለምድ : ኀዲገ : ገቢረ : ሠናይ : አው : ዘየኀ

የሚገባው : ነውና ። እንደዚህ : ካለው : መብል : ከእርሱ : ጋር : የሚበላ : ሰው : እንዴት : ቄስ : ይባላል ? ።

፪፻፳፩ በስ : ፻፩ ። ከቀሳውስት : አንዱ : ስንኳ : አባቶቻችን : ሐዋርያት : ከሠሩት : ሥርዓት : የወጣ : ሥርዓት : ለሕዝቡ : አያጽናባቸው ። ሉቃስ : እንዲህ : አለ ። (የሐዋ : ፲፭ : ፲) ። እግዚአብሔርን : ለምን : ትፈታተኑታላችሁ ። እኛና : አባቶቻችን : እንሸከመው : ዘንድ : ያልቻል ነውን ፤ ለተማሪዎቹ : በአንገታቸው : ሸክምን : ታሸከሚቸዋላችሁ ። ወደ : እግዚአብሔር : በተመለሱ : ምእመናን : ላይ : ሥርዓት : እንዳታጸኑባቸው : እኔ : አፈርዳለሁ ። እነሆ : መንፈስ : ቅዱስ : ወደደ ። እኛም : በናንተ : ላይ : ሥርዓት : እንዳናጸና ፤ ልታደርጉትም : የማይገባውን : እንዳናዛችሁ : ወደድን ።

፪፻፳፪ በስ : ፻፪ ። ከሰው : ወገን : በማናቸውም : ፊት : ቄሱ : ፈጽሞ : አይራቆት ። በችግር : ጊዜ : ካልሆነ : በቀር ። ቢቸግረው : ግን : ወደ : መዋትም : (ወሸባ : ቤት) : ሊሄድ : ቢወድ : ሕዝቡ : ሳይሰበሰቡ : ብቻቸውን : በመዓርግ : እንደ : እርሱ : ካሉት : ጋር : ይሂድ ።

፪፻፳፫ ኒቅያ : ፻፫ ። ቀሳውስት ወደ : ኤጲስቆጶሳቸው : በዓመት : ፪ : ጊዜ : ይሰብሰቡ ። ለእርሱ : የሚገባውንም : ሁሉ : ይመርምሩ ።

፪፻፳፬ አምስተኛ : ክፍል : ከሹመቱ : የሚሻርበትን : ምክንያት : የሚናገር : ነው ። ይህችውም : ተጽፋ : መኖርዋና : ቍጥሯ : በአንቀጸ : ኤጲስቆጶሳት : (ፍት : ፳ : ፪፻፳፪) ። የተነገረላት : ናት ። ሁለመናውም : ይህ : ነው ። መማለጃ : ሰጥቶ : የተሾመ : ቄስ : ሁሉ : ይሻር ። ወይም : በማስፈራራት : ወይም : በማድላት : በተንኰል : ወይም : መማለጃ : እሰጣለሁ : ብሎ : የተሾመ ፤ ይሻር ። ወይም ፤ ሁለት : ጊዜ : የተሾመ ፤ ወይም : ሁለት : ሚስት : ያገባ ፤ ወይም : ሕዝቡን : ከማስተማር : ቸል : የሚል ፤ ወይም ፤ ነዳያን : ካህናትን : ቸል : የሚላቸው ፤ የማይረዳቸውም ፤ ወይም : የኃጢአተኛውን : ንስሐ : የማይቀበል ፤ ወይም : በነገር : ሠረንትና : ሐሰትን : በመመስከር : የታወቀ : የሚታበይ ፤ ሕግን : አውቆ : የማይሠራባት : ወይም : ዘወትር : የሚለከር : ክፉ : ሥራንም : የሚያዘወ

ሥሥ ፡ ርዩ ፡ እምዘለቅሐ ፡ አው ፡ ዘሰከበ ፡ ምስለ ፡ ብእሲት ፡ ዘማዊት ፡ ወእመኒ ፡ ኮነት ፡ ዘተሐበያ ፡ አው ፡ ዘይመስሎሙ ፡ አው ፡ ዘየሐውር ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ዘእንበለ ፡ ትእዛዘ ፡ ሊቁ ፡ አው ፡ ዘይዘብጥ ፡ መነሂ ፡ ከመ ፡ ይፍርህዎ ፡ ሰብእ ። አው ፡ ዘይትአመን ፡ በሐሳበ ፡ ክዋክብት ፡ ወዘየአምን ፡ ነገረ ፡ ጠንቋልያን ፡ ወመሠርያን ፡ አው ፡ ዘተወክፈ ፡ ጥምቀተ ፡ ዓላውያን ፡ አው ፡ ዘይትሜጦ ፡ ቍርባኖሙ ፡ አው ፡ ዘይጼሊ ፡ ምስሌሆሙ ።

ትር ፡ በጎ ፡ አለመሥራትን ፡ የለመደ ፡ ከአበደረው ፡ ላይ ፡ ትርፍን ፡ የሚፈልግ ፡ ከዘማዊት ፡ ሴት ፡ ጋር ፡ የተኛ ፡ ተያዥ ፡ የሆናትም ፡ ብትሆን ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ የሠራ ፡ ወይም ፡ አለቃው ፡ ሳይፈቅድለት ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ የሚሄድ ፡ ወይም ፡ ሰዎች ፡ ይፈሩት ፡ ዘንድ ፡ ማንንም ፡ የሚማታ ፡ ኮከብ ፡ በመቍጠር ፡ የሚታመን ፡ የጠንቋዮችን ፡ ነገር ፡ ሥር ፡ የሚምሱትንም ፡ የሚያምን ፡ የመናፍቃንን ፡ ጥምቀት ፡ የተቀበለ ፡ ወይም ፡ ቍርባናቸውን ፡ የተቀበለ ፡ ወይም ፡ ከነርሱ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ የሚጸልይ ፡ ቄስ ፡ ይሻር ።

፪፻፳፫ ወእምኔሃ ፡ ዘተነግረ ፡ በአንቀጸ ፡ ካህናት ፡ ወዘተጋብአ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ይሰደድ ፡ አው ፡ ይትሙተር ፡ ወዘሂ ፡ ሐጸወ ፡ ርእሶ ፡ አው ፡ ተረክበ ፡ በዝሙት ፡ አው ፡ በሰረቅ ፡ አው ፡ በመሐላ ፡ ሐሰት ፡ አው ፡ ዘየአምን ፡ ከመ ፡ ሕገ ፡ ሰብሳብ ፡ ወበሊዐ ፡ ሥጋ ፡ ወሰትየ ፡ ወይን ፡ ሕሩም ፡ ውእቱ ። አው ፡ ዘይበልዕ ፡ በውስተ ፡ ምሥያጣት ፡ ወዘይሰቲ ፡ ውስተ ፡ ምርፋቃት ፡ ወዘይበልዕ ፡ ምዉተ ፡ አው ፡ ብላዐ ፡ አርዌ ፡ አው ፡ ዘይበውእ ፡ ምኵራበ ፡ አይሁድ ፡ አው ፡ ዘይበውእ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖሙ ፡ ለዓላውያን ፡ ለተፈውሶ ፡ አው ፡ ዘይጸውም ፡ ምስለ ፡ አይሁድ ፡ ወይበልዕ ምስሌሆሙ ። አው ፡ ዘይነሥእ ፡ አምኃ ፡ ዘበዓላቲሆሙ ፡ አው ፡ ዘይፌኑ ፡ ኀበ ፡ ምኵራባቲሆሙ ፡ አው ፡ ኀበ ፡ መካናቲሆሙ ፡ ለእለ ፡ ኢየአምኑ ፡ አው ፡ ኀበ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናቲሆሙ ፡ ለዕልዋን ፡ ሃይማኖት ፡ ዘይወስድ ፡ አምኃ ፡ አው ፡ ዘይትናገር ፡ ምስለ ፡ ውጉዝ ፡ አው ፡ ምስለ ፡ ዘተሰደ ፡ አው ፡ ዘይጼሊ ፡ ምስሌሁ ፡ አው ፡ ዘይነግድ ፡ ዘእንበለ ፡ መጽሐፈ ፡ መባሕተ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዚአሁ ።

፪፻፳፫ ክርስዋም ፡ በአንቀጸ ፡ ካህናት ፡ የተነገረ ፡ ነው ።(ፍ፡ነ፡፫፻፲፮) ከዚህም ፡ የተሰበሰበ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ይለይ ፡ ወይም ፡ ይሻር ፡ ዘንድ ። ራሱን ፡ ጃንደረባ ፡ ያደረገ ፡ ወይም ፡ በዝሙት ፡ የተገኘ ፡ ወይም ፡ ሲሰርቅ ፡ የተገኘ ፡ ወይም ፡ በሐሰት ፡ የማለ ፡ የጋብቻ ፡ ሥራት ፡ ሥጋ ፡ መብላትና ፡ ወይን ፡ መጠጣት ፡ አይገባም ፡ የሚል ፡ ወይም ፡ በገበያ ፡ መካከል ፡ የሚበላ ፡ ከመሸታ ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ የሚጠጣ ፡ ሞቶ ፡ የበከተውን ፡ ቍርጥራጩን ፡ ወይም ፡ የአውሬውን ፡ ትራፊ ፡ የሚበላ ፡ ወይም ፡ ፈውስ ፡ አገኛለሁ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ መናፍቃን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚገባ ፡ ወይም የአይሁድን ፡ ጾም ፡ የሚጾም ፡ ከነርሱም ፡ ጋር ፡ የሚበላ ፡ የበዓላቸውንም ፡ አጅ ፡ መንሻ ፡ የሚቀበል ፡ ወይም ፡ ወደምኵራባቸው ፡ ወይም ፡ ወደማያምኑ ፡ ሰዎች ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ ሃይማኖትን ፡ ወደካዱ ፡ ሰዎች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እጅ መንሻ ፡ የሚወስድ ፡ ወይም ፡ ተወግዞ ፡ ከተለየው ፡ ጋር ፡ የሚናገር ፡ ከተለየውም ፡ ጋር ፡ የሚጸልይ ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ ፈቃድ ፡ የሚሄድ ፡ ይሻር ።

፪፻፳፬ ወእምኔሃ ፡ ዘተነግረ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ አንቀጽ ፡ ወውእቱ ፡ ፲፡፱፡ ፆ፡፱ ። ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ረስጠብ ፡ ፫ቱ ፡ ወለእመ ፡ ተፈልጠ ፡ ቀሲስ ፡ አው ፡ ዲያቆን ፡ እምነ ፡ ብእሲቱ ፡ በምክንያተ ፡ ተልእኮቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኢይደልዎ ፡ ተፈልጦ ። ወእመሰ ፡ ኀደጋ ፡ ለብእሲቱ ፡ በዘንቱ ፡ ምክንያት ፡ ይትመተር ። ረስጠጅ ፡ ፳ ፡ ወከማሁ ፡ ለእመ ፡ አውፅአ ፡ በምክንያተ ፡ ጽሙና ፡ ወምንኵስና ።

፪፻፳፬ ከእርስዋ ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ የተነገረው ፡ ይህ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ፲ወገን ፡ ነው ። ከነርሱ ፡ አንዱ ፡ ረስጠብ ፡ ፫ ። እግዚአብሔርን ፡ በማገልገል ፡ ምክንያት ፡ ቄስ ፡ ወይም ፡ ዲያቆን ፡ ከሚስቱ ፡ ቢለይ ፡ መለየት ፡ አይገባውም ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ሚስቱን ፡ ቢፈታት ፡ ይሻር ። ረስጠጅ ፡ ፳ ። እንደዚሁም ፡ በምንኵስናና ፡ በተባሕትዎ ፡ ምክንያት ፡ ቢፈታት ፡ ይሻር ።

፪፻፳፭ ወዳግም ፡ ረስጠብ ፡ ፲ወ፱ቱ ፡ ጾከ ፡ ፬ቱ ፡ እመበ

፪፻፳፭ ሁለተኛ ፡ ረስጠብ ፡ ፲፱ ። ጾከ ፡ ፬ ። በታወቀች ፡

ቀሲስ ፡ እው ፡ ዲያቆን ፡ ዘተሥዕረ ፡ በርትዕ ፡ በእንተ ፡ ኃጢአቱ ፡ ከሥት ፡ ወእምዝ ፡ ተሐበለ ፡ ላዕለ ፡ ግብረ ፡ መልእክት ፡ እንተ ፡ ኮነት ፡ ሎቱ ፡ በዘመነ ፡ እብራቱ ፡ ይትፈለጥ ፡ እምቤተ፡ ክርስቲያን ፡ ፍጹመ ። ወከማሁ ፡ ኵሉ ፡ ዘአእመረ ፡ ግብሮ ፡ ወተደመረ ፡ ምስሌሁ ።

፪፻፹፫ ሣልስ ፡ ረስጠብ ፡ ዘ፳ወ፪ቱ ፡ ጾክ ፡ ፰ቱ ፡ ወለእመ ፡ መነኖ ፡ ቀሲስ ፡ እው ፡ ዲያቆን ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ዚአሁ ፡ ወገብረ ፡ ሎቱ ፡ ምሥዋዐ ፡ በባሕቲቱ ፡ ወጸውዖ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ፪ተ ፡ ጊዜያተ ፡ እው ፡ ፫ተ ፡ ወኢተሰጥዎ ፡ ይትመተር ፡ እመዓርጊሁ ፡ ውእቱኒ ፡ ወእለ ፡ ተለውዎ ።

፪፻፹፬ ራብዕ ፡ ረስጣ ፡ ፲ወ፩ቱ ፡ ኒቅያ ፡ ፲ወ፩ቱ ፡ ወለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ቀሲስ ፡ እው ፡ ካህን ፡ አው ፡ መነኮስ ፡ ከመ ፡ ይሑር ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ኢትትወከፎ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ካልእት ፡ እላ ፡ ያገብርዎ ፡ ከመ ፡ ይትመየጥ ፡ ኀበ ፡ መካኑ ። ወለእመ ፡ አበየ ፡ ተመይጦ ፡ ይሰደድ ፡ ወኢይደመር ፡ ኀበ ፡ ጉባኤ ።

፪፻፺ ዘ፲ወ፫ቱ ፡ ወለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ይሑር ፡ እምሥዋዑ ፡ ኀበ ፡ ካልእ ፡ ምሥዋዕ ፡ ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ ጸልእዎ ፡ እለ ፡ ኮኑ ፡ ውስቴታ ፡ ወካዕበ ፡ ሶበ ፡ ፈቀደ ፡ ተመይጦ ፡ ኀበ ፡ መካን ፡ ዘፈለሰ ፡ እምኔሁ ፡ ኢይትወከፍዎ ፡ እልክቱ ፡ እምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ዳእሙ ፡ ይሠዓር ፡ ሚመቱ ፡ በህየኒ ፡ ወበዝየኒ ። ረስጠብ ፡ ዘ፲ወ፪ቱ ፡ ወፈድፋደሰ ፡ ለእመ ፡ ፈነወ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ኀቤሁ ፡ መልእክተ ፡ ከመ ፡ ይትመየጥ ፡ ኀበ ፡ መካኑ ፡ ለእመ ፡ ኢሰምዐ ።

፪፻፺፩ ኃምስ ፡ ዘኒቅያ ፡ ፳ወ፯ቱ ፡ ወኢይስድዱ ፡ ቀሳውስት ፡ ሕዝበ ፡ እምእመናን ፡ እምነ ፡ ቍርባን ፡ በምክንያተ ፡ ቍጥዓ ፡ እው ፡ በምንትኒ ፡ ግብር ፡ እምግብረተ ፡ ዓለም ፡ ወዘገብረ ፡ ዘንተ ፡ ይደቅ፡ እመዓርጊሁ ፡ ወይከልእዎ ፡ ትድምርተ ፡ ምእመናን ።

፪፻፺፪ ሳድስ ፡ ዘኒቅያ ፡ ፱ቱ ፡ ወእመ ፡ ተሠይመ ፡ ፩ዱ ፡ ቅስና ፡ እንበለ ፡ ይሕትቱ ፡ ምግባሮ ፡ ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ ተዐውቀት ፡ ኃጢአቱ ፡ እንተ ፡ ገብሩ ፡ ይሰደድ ፡ ውእቱ ፡ ወበውሳኔሂ ፡ ኢትትወከፎ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

፪፻፺፫ ሳብዕ ፡ ቀጠጅ ፡ ፱ቱ ፡ ወለእመ ፡ ኢተእመነ ፡ ኃጢአቶ ፡ ወእምዝ ፡ ዘለፍዎ ፡ በርትዕ ፡ ከሡት፡



ኃጢአቱ ፡ በእርግጥ ፡ የተሻረ ፡ ቄስ ፡ ወይም ፡ ዲያቆን ፡ ቢኖር ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ቀድሞ ፡ ሳይሻር ፡ በሰሞኑ ፡ ወራት ፡ ይሠራው ፡ የነበረውን ፡ የአገልግሎት ፡ ሥራ ፡ ተደፋፍሮ ፡ ቢሠራ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ፈጽሞ ፡ ይለይ ፡ ሥራውንም ፡ እያወቀ ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ ይሻር ።

፪፻፹፫ ሦስተኛ ፡ ረስጠብ ፡ ፳፪ ። ጾክ ፡ ፰ ። ቄስ ፡ ወይም ፡ ዲያቆን ፡ ኤጲስቆጶሱን ፡ ቢንቀው ፡ ብቻውንም ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ቢሠራ ፡ ኤጲስቆጶሱም ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ቢጠራው ፡ መልስ ፡ ባይሰጠው ፡ እርሱ ፡ ከማዕርጉ ፡ ይሻር ። ተከታዮቹም ፡ ይሻሩ ።

፪፻፹፬ አራተኛ ፡ ረስጣ ፡ ፲፩ ። ኒቅያ ፡ ፲፩ ። ቄስ ፡ ወይም ፡ ካህን ፡ ወይም ፡ መነኵሴ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ ትቶ ፡ ቢሄድ ፡ ሌላይቱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አትቀበለው ፡ ወደ ፡ ቦታው ፡ ይመለስ ፡ ዘንድ ፡ ይግልጹት ፡ እንጂ ። ሊመለስም ፡ ባይወድ ፡ ይለይ ። በጉባኤም ፡ አይቀላቀል ።

፪፻፺ ፲፫ ። ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሊሄድ ፡ ቢወድ ፡ በዚያች ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ ያሉትም ፡ ሰዎች ፡ ቢጠሉት ፡ ዳግመኛም ፡ ወደ ፡ ተወው ፡ ቦታ ፡ ሊመለስ ፡ ቢወድ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እነዚያ ፡ አይቀበሉት ፡ በዚህም ፡ በዚያም ፡ ሹመቱ ፡ ይሻር ፡ እንጂ ። ረስጠብ ፡ ፲፪ ። ይልቁንም ፡ ኤጲስቆጶሱ ወደርሱ ፡ መልእክት ፡ ቢልክ ፡ ወደ ፡ ቦታውም፡ ይመለስ ፡ ዘንድ ፡ ባይሰማ ፡ ይሻር ።

፪፻፺፩ አምስተኛ ፡ ኒቅያ ፡ ፳፯ ። ቀሳውስት ፡ ከምእመናን ፡ ወገን ፡ እንዱንስ ፡ እንኳ ፡ በቍጣ ፡ ወይም ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ሥራ ፡ በማናቸውም ፡ ሥራ ፡ ምክንያት ፡ አይከልክሉ ። ይህን ፡ ያደረገ ፡ ከሹመቱ ፡ ይሻር ። ከምእመናንም ፡ አንድነት ፡ ይለዩት ።

፪፻፺፪ ስድስተኛ ፡ ኒቅያ ፡ ፱ ። ሥራውን ፡ ሳይመረምሩ ፡ እንዱ ፡ ቅስና ፡ ቢሾም ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የሠራት ፡ ኃጢአት ፡ ብትታወቅ ፡ እርሱ ፡ ይለይ ። በጉባኤውም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አትቀበለው ።

፪፻፺፫ ሰባተኛ ፡ ቀጠጅ ፡ ፱ ። ኃጢአቱን ፡ ባያምን ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በሚገባ ፡ ገልጠው ፡ ከዘለፉት፡

አ.ይደልዎ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይትሰአክ ፡ በግብረ ፡ ክህነት ፡ ግሙራ ፡ ወለእመሰ ፡ እምነ ፡ ውእቱ ፡ በርእሱ ፡ አ.መናትው ፡ ሎቱ ፡ ተልእኮ ፡ ዘእን በለ ፡ ቀሪበ ፡ ቍርባን ፡ ባሕቲቱ ።

፪፻፴፩ ሳምን ፡ ዘኒቅያ ፡ ኗወ፳ቱ ፡ ኢይባኡ ፡ ቀሳው ስት ፡ ወእሊአሆሙ ፡ ኀበ ፡ ተሐብዮ ፡ ወኢይኩኑ ስምዐ ፡ በውዴት ፡ ወኢይሑሩ ፡ ለአስተዋድዮ ፡ ሰብእ ፡ ኀበ ፡ ነገሥት ፡ ወኢይኩኑ ፡ ሐማይያን ፡ ወኢፈቃድያነ ፡ እከይ ፡ ለምእመናን ፡ ወዘገ ብረ ፡ ዘንተ ፡ እምኔሆሙ ፡ ይረድ ፡ እመዓርጊሁ ፡ ወይስደድ ፡ እምትባኤ ።

፪፻፴፪ ታስዕ ፡ ዘኒቅያ ፡ ኗወ፱ቱ ፡ ወለእመ ፡ ተዐደወ ፡ ፩ሂ ፡ እምቀሳውሳት ፡ ወዲያቆናት ፡ ወአብአ ፡ ብእሲተ ፡ ትክተ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወመጠዋ ፡ ላቲ ፡ ቍርባነ ፡ በመዋዕለ ፡ ትክ ቶሃ ፡ ይደቅ ፡ እመዓርጊሁ ፡ ወእመኒ ፡ ኮነት ፡ እምአንስትያ ፡ ነገሥት ።

፪፻፴፫ ዓሥር ፡ ዘኒቅያ ፡ ፲ወ፰ቱ ፡ ለቀሳውስት ፡ ወዲያ ቆናት ፡ ሶበ ፡ ወፅኡ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያናቲ ሆሙ ፡ ኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይትወከፍዎሙ ፡ ቤተ፡ ክርስቲያናት ፡ አላ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይንግሩ ፡ ኵሎ ፡ ምክንያተ ፡ መፍቀዶሙ ፡ እስከ ፡ ይት መየጡ ፡ ኀበ ፡ ማኅደሪሆሙ ። ወሶበ ፡ ኢሖሩ ፡ ወኢተመይጡ ፡ ኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይሳተፍ ዎሙ ። ወለእመ ፡ ኀደገ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ በፈቃዱ ፡ ባሕቲቱ ፡ ወለ እመ ፡ ኢኮነ ፡ በተስናእዎተ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ምስ ሌሁ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ትሥዓር ፡ ክህነቱ ።

፪፻፴፬ ክፍል ፡ ሳድስ ፡ ዘኢይትከላእ ፡ እምተልዕኮተ ፡ መዓርግ ።
በደስ ፡ ፳ቱ ፡ ቀሲስ ፡ ሶበ ፡ ወለደት ፡ ብእሲቱ ፡ ኢይትከላእ ።

፪፻፴፭ ፱ቱ ፡ ወሶበ ፡ ሖረ ፡ ውኅደረ ፡ ኀበ ፡ መካነ ፡ ዘኢ ኮነ ፡ ሎቱ ፡ ወተወከፍዎ ፡ ካህናተ ፡ ውእቱ ፡ ብሔር ፡ ይስአልዎ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ዚአሁ ፡ ከመ ፡ ኢይኩን ፡ ዘጕየ ፡ ወለእመሰ ፡ ኮነት ፡ ሀገሩ ፡ ርኅቅተ ፡ ለይትመከር ። ለእመ ፡ ኮነ ፡ ረድአ ፡ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ይሳተፍዎ ፡ ወየ ሀብዎ ፡ ክብረ ፡ ምክሕቢቲ ።



የክህነትን ፡ ሥራ ፡ ፈጽሞ ፡ መሥራት ፡ አይገባ ውም ። እርሱ ፡ ራሱ ፡ ቢያምን ፡ ግን ፡ ሥጋው ንና ፡ ደሙን ፡ ከመቀበል ፡ በቀር ፡ በክህነቱ ፡ ማገልገል ፡ አይገባውም ።

፪፻፴፩ ስምንተኛ ፡ ኒቅያ ፡ ኟ፰ ። ቀሳውስትና ፡ ዲያቆ ናት ፡ ወደ ፡ ዋስነት ፡ አይግቡ ። በነገር ፡ ሥራ ፡ አይመስክሩ ። ሰውንም ፡ ለመክሰስ ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ አይሂዱ ። ሐሜተኞች ፡ አይሁኑ ። ለም እመናንም ፡ ክፋትን ፡ አይውደዱ ። ከነርሱ ፡ ወገን ፡ ይህን ፡ ያደረገ ፡ ከሹመቱ ፡ ይሻር ፡ ከጉ ባኤም ፡ ይሰደ ።

፪፻፴፪ ዘጠኝኛ ፡ ኒቅያ ፡ ኟ፱ ። ከቀሳውስትና ፡ ከዲያቆ ናት ፡ ወገን ፡ አንዱስ ፡ እንኳ ፡ ተደፋፍሮ ፡ ከግ ዳጅዋ ፡ (ከደሟ) ፡ ያልነጻችውን ፡ ሴት ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያስገባ ፡ በደሟም ፡ ወራት ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ያቀበላት ፡ ቢኖር ፡ ከሹ መቱ ፡ ይሻር ። ምንም ፡ ከነገሥታት ፡ ሴቶች ፡ ወገን ፡ ብትሆን ።

፪፻፴፫ አሥረኛ ፡ ኒቅያ ፡ ፲፰ ። ቀሳውስትና ፡ ዲያቆ ናት ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያናቸው ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሊቀበሏቸው ፡ አይገባም ፡ ወደ ፡ ቦታቸው ፡ እስኪመለሱ ፡ ድረስ ፡ የፈቃዳቸውን፡ ምክንያት ፡ ሁሉ ፡ ይናገሩ ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ፡ እንጂ ። ባይመለሱ ፡ ግን ፡ ሊቀበሏቸው ፡ አይ ገባም ። ከነርሱ ፡ አንዱ ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ ቤተ፡ ክርስቲያኑን ፡ ቢተው ፡ ከነርሱ ፡ ጋር ፡ ባለው ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ፈቃድ ፡ ካልሆነ ፡ ስለዚህ ፡ ክህ ነቱ ፡ ይሻር ።

፪፻፴፬ ክፍል ፡ ፮ ። በማዕርጉ ፡ ከአገልግሎት ፡ የማይከ ለከልበትን ፡ ይናገራል ።
በደስ ፡ ፳ ። ቄስ ፡ ሚስቱ ፡ በወለደች ፡ ጊዜ ፡ አይከለከል ።

፪፻፴፭ ፱ ። ቦታው ፡ ወዳይደለ ፡ ቦታ ፡ ሄዶ ፡ ቢሰነብት፡ የዚያ ፡ አገር ፡ ካህናትም ፡ ቢቀበሉት ፡ ኮብሎ ፡ የመጣ ፡ እንዳይሆን ፡ የአገሩን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ይጠይቁት ። አገሩ ፡ ሩቅ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ አገል ጋይ ፡ እንደሆነ ፡ ይፈትን ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ይቀ በሉት ። እጥፍ ፡ ክብርም ፡ ይስጡት ።

## አንቀጽ ሳብዕ ።

### በእንተ ፡ ዲያቆናት ።

፲፻፹፱ ወውእቱ ፡ ፫ቱ ፡ አክፋል ። ክፍል ፡ ቀዳማዊ ፡ በእንተ ፡ ትእዛዛት ፡ ድልዋት ፡ ይቤ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ እምድኅረ ፡ አንብሮቱ ፡ ትእዛዘ ፡ ለቀሳውስት ። ጤት ፡ ፩ቱ ፡ ወዲያቆናትኒ ፡ ካዕበ ፡ ከማሁ ፡ ለይኩኑ ፡ ህዱአነ ፡ ወተአዛዝያነ ፡ ወኢይኩኑ ፡ ተናጋርያነ ፡ በ፪ቱ ፡ ልሳን ፡ ወኢይጽንኑ ኅበ ፡ ብዝኀ ፡ ስትየ ፡ ወይን ፡ ወኢያፍቅሩ ፡ መክፈልተ ፡ ረባኅ ፡ ርኩስ ፡ አላ ፡ ይትአኀዙ ፡ በምሥጢረ ፡ ሃይማኖት ፡ በሕሊና ፡ ንጹሕ ፡ ወትፍሥሕተ ፡ ገጽ ፡ ብዙኀ ፡ ወትእዛዝ ፡ በእንተ ፡ እሉ ፡ ይትመከሩ ፡ ቅድመ ፡ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ይትለአኩ ፡ ለእመ ፡ ኮኑ ፡ ዘእንበለ ፡ ነውር ። ወይኩን ፡ ዲያቆን ፡ ዘአሐተ ፡ ብእሲተ ፡ አውሰበ ፡ ዘያሤኒ ፡ ሠሪዐ ፡ ቤቱ ፡ ወውሉዱ ፡ እስመ ፡ እለ ፡ ያሤንዩ ፡ ተልእኮተ ፡ ይረብሑ ፡ ለነፍሶሙ ፡ መዓርገ ፡ ሠናየ ፡ ወሞገስ ፡ ፍድፉደ ፡ ለነፍሶሙ ። በእንተ ፡ ሃይማኖተ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

፲፻፺ ረስጣ ፡ ፲ወ፮ቱ ፡ ይቤ ፡ ማቴዎስ ፡ ወዲያቆናት ፡ ይሠየሙ ፡ በከመ ፡ ጽሑፍ ፡ በሰምዐ ፡ ፪ቱ ፡ ወ፫ቱ ፡ ሰማዕት ፡ ይቁም ፡ ኵሉ ፡ ነገር ፡ ወይትፈተኑ ፡ በኵሉ ፡ ተልእኮ ። ወስምዐ ይኩንዎሙ ጉባኤ ፡ ከመ ፡ እሙንቱ ፡ ነበሩ ፡ ምስለ ፡ እሐቲ ፡ ብእሲት ፡ ወአልሀቁ ፡ ውሉዶሙ ፡ በንጽሕ ፡ ወይኩኑ ፡ መሓርያነ ፡ ወየዋሃነ ፡ ወእኮ ፡ መንጐራጕራነ ፡ ወኢ ፡ ዘ፪ኤ ፡ ልሳናት ፡ ወኢመዓትማነ ፡ እስመ ፡ መዓት ፡ ያማስን ፡ ብእሴ ፡ ጠቢበ ። ወኢይኩኑ ፡ ዘያደልዉ ፡ ለገጸ ፡ አብዕልት ፡ ወዘይገፍዑ ፡ ነዳያነ ፡ ወዘያበዝኁ ፡ ስትየ ፡ ወይን ፡ ወኢይጸምዉ ፡ በእንተ ፡ ምሥጢራት ፡ ሠናያት ፡ ወየአዝዝዎሙ ፡ ለእለ ፡ ቦሙ ፡ ንዋይ ፡ እምእኀው ፡ ከመ ፡ ይጸግውዎሙ ፡ ለእለ ፡ እልቦሙ ፡ ንዋይ ፡ ወይሳተፍዎሙ ፡ በውሂብ ፡ ወያከብሩ ፡ ጉባኤ ፡ በኵሉ ፡ ክብር ፡ ወኅፍረት ፡ ወፍርሃተ ፡ እግዚአብሔር ።

፲፻፺፩ ክፍል ፡ ዳግም ፡ በእንተ ፡ ሢመተ ፡ ዲያቆናት ። ረስጣ ፡ ፶ወ፩ቱ ፡ ቀጠጅ ፡ ፲ወ፩ቱ ፡ ሶበ ፡ ትሠይሞ ፡ ለዲያቆን ፡ እንብር ፡ እዴከ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወጸሊ ፡ ወቀሳውስት ፡ ኵሎሙ ፡ ወዲያቆናትኒ ፡



## አንቀጽ ፡ ፯ ።

### ስለ ፡ ዲያቆናት ።

፲፻፹፱ ይኸውም ፡ ፫ ፡ ክፍል ፡ ነው ። መጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ ስለሚገቡ ፡ ትእዛዛት ፡ ይናገራል ። ጤት ፡ ፩ ። ዳግመኛም ፡ እንደዚሁ ፡ ዲያቆናት ፡ ጸጥ ፡ ያሉ ፡ የሚታዘዙ ፡ ይሁኑ ። በሁለት ፡ አንደበት ፡ የሚናገሩ ፡ አይሁኑ ። ወይን ፡ አብዝቶ ፡ ወደ ፡ መጠጣት ፡ አያዘንብሉ ። ርኩስ ፡ የሆነውን ፡ የትርፍ ፡ ድርሻ ፡ አይውደዱ ። በንጹሕ ፡ ሐሳብ ፡ በሃይማኖት ፡ ምሥጢር ፡ በብዙ ፡ ፍሥሐ ፡ ገጽ ፡ በመታዘዝ ፡ ይወሰኑ ፡ እንጂ ። ስለ ፡ እሊህ ፡ አስቀድመው ፡ ይፈተኑ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ነውር ፡ የሌለባቸው ፡ ከሆኑ ፡ ያገልግሉ ። ዲያቆን ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ያገባ ፡ ቤተ ፡ ሰቦቹንና ፡ ልጆቹን ፡ በሚገባ ፡ የሚያስተዳድር ፡ ይሁን ። ማገልገልን ፡ የሚያሳምሩ ፡ ለሰውነታቸው ፡ በጎ ፡ ማዕርግን ፡ ያገኛሉና ። ይልቁንም ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለሚያምኑ ፡ ባለሟልነትን ፡ ለሰውነታቸው ፡ ያገኛሉ ።

፲፻፺ ረስጣ ፡ ፲፮ ። ማቴዎስ ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ዲያቆናትም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በሁለት ፡ በሦስት ፡ ምስክር ፡ ይጸናል ፡ ተብሎ ፡ በተጻፈው ፡ መሠረት ፡ ይሾሙ ። በአገልግሎት ፡ ሁሉ ፡ ይፈተኑ ። ከአንዲት ፡ ሴት ፡ ጋር ፡ እንደኖሩ ፡ በንጽሕና ፡ ልጆቻቸውን ፡ እንዳሳደጉ ፡ የተሰበሰቡት ፡ ምስክር ፡ ይሁኑዋቸው ። የሚራሩ ፡ የዋሃን ፡ የማያንጐራጕሩ ፡ ይሁኑ ። ሁለት ፡ አንደበትም ፡ አይሁኑ ። ቍጡዎች ፡ አይሁኑ ። ቍጣ ፡ አዋቂውን ፡ ሰው ፡ ያጠፋልና ። ለባለጸጎች ፡ ፊት ፡ የሚያደሉ ፡ ነዳያንን ፡ የሚያሳዝኑ ፡ ወይን ፡ አብዝተው ፡ የሚጠጡ ፡ አይሁኑ ። ስለ ፡ በጎ ፡ ምሥጢራት ፡ ምርመራ ፡ የሚሰንፉ ፡ አይሁኑ ። ከወንድሞች ፡ ወገን ፡ ገንዘብ ፡ ያላቸውን ፡ ሰዎች ፡ ገንዘብ ፡ ለሌላቸው ፡ ይሰጧቸው ፡ ዘንድ ፡ ይዘዟቸው ። በመስጠትም ፡ ይተባበሩዋቸው ። በፍጹም ፡ ክብርና ፡ ኃፍረት ፡ እግዚአብሔርንም ፡ በመፍራት ፡ ጉባኤውን ፡ ያከብሩ ።

፲፻፺፩ ክፍል ፡ ፪ ። ስለ ፡ ዲያቆናት ፡ ሹመት ፡ ይናገራል ። ረስጣ ፡ ፶፩ ። ቀጠጅ ፡ ፲፩ ። ዲያቆኑን ፡ በምትሾምበት ፡ ጊዜ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ እጅህን ፡ አስቀምጥና ፡ ጸልይ ፡ ሁሉም ፡ ቀሳውስትና ፡

እንዘ ፡ ይቀውሙ ፡ ዘሸወ፫ቱ ፡ ወይትነረይ ፡ በከመ ፡ እቅደምነ ፡ ነገረ ፡ ወንቤ ። ወእምዝ ፡ ይደይ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ባሕቲቱ ፡ እዴሁ ፡ ላዕሌሁ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ኢይሠየም ፡ ከመ ፡ ይትመጦ ፡ መንፈስ ፡ ዐበይ ፡ ዝንቱ ፡ ዘይሳተፍዎ ፡ ቀሳውስት ፤ አላ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ትእዛዘተ ፡ ኤጲስ ቆጶስ ።

፩፻፵፪ ቀጠሮ ፡ ፲ወ፩ዱ ፡ ሥርዋጽ ፡ በመጽሐፈ ፡ ሮማ ውያን ፡ ንቡር ፡ ወይቤ ፡ ኢይሠየም ፡ ዲያቆን ፡ ቅድመ ፡ ይኩን ፡ መዋዕሊሁ ፡ ፳ወ፭ቱ ፡ ዓመት፡ ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ለዲያቆን ፡ በውስተ ፡ ሕግ ፡ ሐዲስ ፡ ወሥርዓቶሙኒ ፡ ለሌዋውያን ፡ ዘሕግ ፡ ብሉይ ። ናሁ ፡ ይኤዝዝ ፡ ከመ ፡ ኢይግበር ፡ ግብራ ፡ ለደብተራ ፡ ዘመን ፡ ለእመ ፡ ኢበጽሐ ፡ ኀበ ፡ ዝንቱ ፡ ዓቅም ። ወኢይትከሀሎ ፡ ለሰብእ፡ ከመ ፡ ይምጽእዎ ፡ ሠናይት ፡ ዘእንበለ ፡ እምድ ኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ሕይወት ፡ ወግብረ ፡ መልእክተ ፡ ዲቁናስ ፡ በውስተ ፡ ሐዲስ ፡ ሕግ ፡ እኮ ፡ ከመዝ

፩፻፵፫ ቀጠሮ ፡ ፲ወ፬ቱ ፡ ወናሁ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩኑ፡ ፯ ፡ ዲያቆናት ፡ ወለእመ ፡ ኢኮነት ፡ ሀገር ፡ ዐባየ ። ወእመሰ ፡ ሀገረ ፡ ዐባየ ፡ ኮነት ፡ ጥቀ ፡ በእምጣነ ፡ ሠምረ ፡ ልበ ፡ ሊቀ ።

፩፻፵፬ ፳ወ፱ ፡ መጽሐፈ ፡ አብረክሲስ ፡ ዘኒቅያ ፡ ፳ወ፯ ፡ ወይሠየሙ ፡ ዲያቆናት ፡ ፯ ፡ በእምጣነ ፡ ይትከ ሀላ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወይሴሰዩ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወካልእንሰ ፡ ይኩኑ ፡ ተእዛዝያን ፡

፩፻፵፭ በስ ፡ ፶ወ፯ቱ ፡ ወይኩን ፡ ዲያቆን ፡ ዘተኀርየ ፡ እምነ ፡ ሠለስቱ ።

፩፻፵፮ ሣልስ ፡ በእንተ ፡ ሥርዓቱ ። ድስቅ ፡ ፴ወ፯ቱ ፡ ወይኩኑ ፡ ካዕበ ፡ ዲያቆናት ፡ ዘእንበለ ፡ ነውር ፡ በእምሳለ ፡ ኤጲስቆጶስ ። ወያክብርዎሙ ፡ ክብረ ፡ ብዙኀ ፡ ወይኩኑ ፡ ፍጹማነ ፡ በክህነቶሙ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዘይክሉ ፡ ገቢረ ፡ ዘእን በለ ፡ ኀፍረት ። ዘ፰ ፡ ወይቁም ፡ ዲያቆን ፡ ዘይትለአኮ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ በንጽሕ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ግብር ፡ ዘእንበለ ፡ ኂስ ፡ ዘከመ ፡ ይትለ እኮ ፡ ለክርስቶስ ፡ ወኢይግበር ፡ ምንተኒ ፡ በፈቃዱ ፡ ዘእንበለ ፡ በሥምረተ ፡ እቡሁ ፡ ዘውእቱ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በኵሉ ፡ ዘይኤዝዞ ፡ ኪያሁ ። ዘ፲ቱ ፡ ወለየሀልዉ ፡ ምስሌክሙ ፡ አ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ቀሳውስት ፡ ወዲያቆናት ፡ ኀበ ፡ መንበረ ፡ ፍትሕ ።



ዲያቆናት ፡ ቁመው ፡ ሳሉ ። ፳፫ ። አስቀድመን ፡ እንደተናገርንና ፡ እንዳልን ፡ ይመረጥ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ብቻ ፡ እጁን ፡ ይጫንበት ። ቀሳውስት ፡ የሚተባበሩትን ፡ ቅስና ፡ ይህ ፡ ዲያ ቆን ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ አይሾምምና ። የኤጲስ ቆጶሱን ፡ ትእዛዝ ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ፤

፩፻፵፪ ቀጠሮ ፡ ፲፩ ። ሥርዋጽ ። በሮማውያን ፡ መጽ ሐፍ ፡ አለ ። ዲያቆን ፡ ፳፭ ፡ ዓመት ፡ ሳይሆ ነው ፡ አስቀድሞ ፡ አይሾም ፡ አለ ። ይህም ፡ በሐ ዲስ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ለዲያቆን ፡ የታዘዘው ፡ ነው ። በብሉይ ፡ ሕግ ፡ ያለው ፡ የሌዋውያንም ፡ ሥርዓት ፡ ከዚህ ፡ ዕድሜ ፡ ካልደረሰ ፡ የደብ ተራ ፡ አሪትን ፡ ሥራ ፡ እንዳይሠራ ፡ ያዛል ፤ ከዚህ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ለሰው ፡ በጎ ፡ ነገሮች ፡ ሊመጡለት ፡ አይቻለ ውም ። የዲቁና ፡ አገልግሎት ፡ ሥራ ፡ ግን ፡ በሐዲስ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ እንደዚህ ፡ አይደለም ።

፩፻፵፫ አገሪቱ ፡ ታላቅ ፡ ካልሆነች ፡ ዲያቆናት ፡ ፯ ፡ ሊሆኑ ፡ ይገባል ። አገሪቱ ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ብትሆን ፡ ግን ፡ አለቃው ፡ እንደወደደ ፡ መጠን፡ ሊሆኑ ፡ ይገባል ።

፩፻፵፬ ፳፱ ፡ መጽሐፈ ፡ አብረክሲስ ። ኒቅያ ፡ ፳፯ ። ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሚቻላት ፡ መጠን ፡ ፯ ፡ ዲያቆናት ፡ ይሾሙ ። ከቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ህብት ፡ ይመገቡ ። ሌሎቹ ፡ ግን ፡ ታዛዦች ፡ ይሁኑ ።

፩፻፵፭ በስ ፡ ፶፯ ። ዲያቆን ፡ ከሦስት ፡ ሰዎች ፡ የተመ ረጠ ፡ ይሁን ።

፩፻፵፮ ፫ተኛ ፡ ስለ ፡ ሥርዓቱ ፡ ይናገራል ። ድስቅ ፡ ፴፯ ። ዳግመኛም ፡ ዲያቆናት ፡ በኤጲስቆጶስ ፡ እምሳል ፡ ያለነውር ፡ ይሁኑ ። ፍጹም ፡ ክብር ንም ፡ ያክብሩዋቸው። ያለ ፡ ኃፍረት ፡ ሥራን ፡ በሚችሉ ፡ ገንዘብ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በክህ ነታቸው ፡ ፍጹማን ፡ ይሁኑ ። ፰ ፡ ኤጲስቆጶሱን፡ የሚያገለግለው ፡ ዲያቆን ፡ በሥራው ፡ ሁሉ ፡ በንጽሕና ፡ ያለ ፡ ነቀፋ ፡ ክርስቶስን ፡ የሚያገለ ግል ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ ጸንቶ ፡ ይኑር ። ያለ ፡ አባቱ ፡ ፈቃድ ፡ ይኸውም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ነው ፡ እርሱን ፡ በሚያዘው ፡ ሁሉ ፡ በፈቃዱ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ አይሥራ ። ፲ ። ኤጲስቆጶሳት ፡ ሆይ ፡ በፍ ርድ ፡ አደባባይ ፡ ቀሳውስትና ፡ ዲያቆናት ፡ አብ ረዋችሁ ፡ ይኑሩ ።

፪፻፵፯ በደስ ፡ ፰ቱ ፡ ወዲያቆንሰ ፡ ከመ ፡ ዘይትለአክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይትለአኮ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ወለቀሳውስት ፡ በኵሉ ፡ ግብር ፡ ወአኮ ፡ በጊዜ ፡ ቅዳሴ ፡ ባሕቲቱ ፡ አላ ፡ ይትለአኮ ፡ ኀበ ፡ ድውያንሂ ፡ ዘሐሙ ፡ እምነ ፡ ሕዝብ ፡ እለ ፡ አልቦሙ ፡ ሐዋጺ ፡ ወያእምሮ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ከመ ፡ ይጸሊ ፡ ሳዕሌሆሙ ፡ አው ፡ ከመ ፡ ይፈኑ ፡ ሎሙ ፡ መፍቅዶሙ ። ወዓዲ ፡ ሰብእ ፡ እለ ፡ በኀቡእ ፡ ጽኑሳን ፡ ወይትለአኮሙ ፡ ለካልአንሂ ፡ እለ ፡ ይመጸውትዎሙ ፡ እመቅደስ ፡ ወመኳንንት ፡ ወያደልዎሙ ፡ ከመ ፡ የሀቡ ፡ ለዕቤራት ፡ ወእጓለ ፡ ማውታ ፡ ወለነዳያን ፡ ወከመዝ ፡ ይፈጽም ፡ ኵሎ ፡ መልእክቶቶ ፡ ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ዘበእማን ፡ ዲያቆን ፡ ዘይቤ ፡ ክርስቶስ ፡ በእንቲአሁ ፡ ወለዘሰሊተ ፡ ተልእከኒ ፡ ያከብሮ ፡ አቡየ ።

፪፻፵፰ ድስቅ ፡ ፲ወ፱ቱ ፡ ወያንብብ ፡ ወንጌለ ፡ እመሂ ፡ ዲያቆን ፡ ወእመሂ ፡ ቀሲስ ፡ ወየሐውጾሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ከመ ፡ ኢይደቅሱ ፡ ወኢይኑሙ ፡ ፩ሂ ፡ አው ፡ ኢይስሐቁ ፡ አው ፡ ከመ ፡ ኢይሳለቁ ፡ ላዕለ ፡ ቢጾሙ ፡ ወይሥርዮሙ ፡ ለሕዝብ ፡ በከመ ፡ ተነግረ ፡ በእንቀጸ ፡ ቅዳሴ ፡ ረስጠብ ፡ ፴ወ፰ቱ ፡ ወይፁር ፡ ጽዋዐ ፡ ለእመ ፡ ኮኑ ፡ ቀሳውስት ፡ ዘኢየአክሉ ፡ በደስ ፡ ፴ወ፩ዱ ፡ ወያቅርብ ፡ ቍርባነ ፡ ለሕዝብ ፡ ሶበ ፡ ተበውሐ ፡ ሎቱ ። ረስጣ ፡ ፴ወ፯ቱ ፡ ወይመጡ ፡ አውሎጊዮ ፡ በእዴሁ ፡ በጊዜ ፡ ምሳሕ ፡ ለእመ ፡ ኢሀሎ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አው ፡ ቀሲስ ፡ ህየ ።

፪፻፵፱ በደስ ፡ ፴ወ፩ቱ ፡ ወአልቦቱ ፡ ለዲያቆን ፡ ሥልጣን ፡ ከመ ፡ ይምሀር ፡ ወያጥምቅ ፡ አው ፡ ይቀድስ ፡ ወይባርክ ፡ ሕዝበ ፡ አላ ፡ ይፀመድ ፡ ለመልእክት ፡ ምስለ ፡ ኤጲሳቆጶስ ፡ አው ፡ ምስለ ፡ ቀሲስ ፡ ወይፈጽም ፡ መልእክተ ፡ ዲቁና ።

፪፻፶ ረስጣ ፡ ፵ወ፫ቱ ፡ ወኢየሀብ ፡ አውሎጊዮ ፡ አላ ፡ ውእቱ ፡ ይነሥእ ፡ እምኤጲስቆጶስ ፡ አው ፡ እም ቀሲስ ፡ ወኢይፁር ፡ ቍርባነ ፡ ወሶበ ፡ ያረ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አው ፡ ቀሲስ ፡ ውእቱሰ ፡ ይመጡ ፡ ጽዋዐ ፡ ለሕዝብ ፡ አኮ ፡ ውእቱ ፡ ካህን ፡ አላ ፡ ላእክ ፡ ካህናት ፡ ጼጥ ፡ ወኢያንብር ፡ እዴሁ ፡ ወኢይመጡ ፡ ቍርባነ ፡ ለዘይትሌዐሎ ፡ አላ ፡ የአዝዝ ፡ ዘይቴሐትዎ ፡ ለመልእክተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

፪፻፵፯ በደስ ፡ ፰ ። ዲያቆን ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንደሚያገለግል ፡ ኤጲስቆጶሱንና ፡ ቀሳውስቱን ፡ በሥራው ፡ ሁሉ ፡ ያገልግል ። በቅዳሴ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ከሕዝቡ ፡ ወገን ፡ ታመው ፡ ጠያቂ ፡ ወዳሌላቸው ፡ ድውያንም ፡ ይላከው ፡ እንጂ ። ይጸልይላቸው ፡ ዘንድ ፡ ወይም ፡ የሚሹትን ፡ ይልክላቸው ፡ ዘንድ ፡ ለኤጲስቆጶሱ ፡ ያስረዳው ። ዳግመኛም ፡ በኅቡእ ፡ ለተቸገሩ ፡ ሰዎች ፡ ከከዘናቱና ፡ ከመኳንንቱ ፡ ወገን ፡ ለሚመጸውቷቸው ፡ ለሌሎችም ፡ ይላካቸው ። ለባልቴቶችና ፡ እናት ፡ አባት ፡ ለሞቱባቸው ፡ ለድሆቹም ፡ ሊሰጡ ፡ ይገባቸዋል ። መልእክቱን ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁ ፡ አድርጎ ፡ ይፈጽም ። እኔን ፡ ያገለገለኝን ፡ አባቴ ፡ ያከብረዋል ፡ ብሎ ፡ ክርስቶስ ፡ የተናገረለት ፡ እውነተኛ ፡ ዲያቆን ፡ ይህ ፡ ነው ። (ዮሐ ፡ ፲፪ ፡ ፳፮) ።

፪፻፵፰ ድስቅ ፡ ፲፱ ። ዲያቆንም ፡ ቢሆን ፡ ቄስም ፡ ቢሆን ፡ ወንጌልን ፡ ያንብብ ። ዲያቆኑም ፡ እንዳያንጐላቹ ፡ እንዳይተኙም ፡ እንዳይስቁ ፡ በባልንጀሮቻቸውም ፡ እንዳይዘብቱ ፡ ሕዝቡን ፡ ይጐብኛቸው ። በእንቀጸ ፡ ቅዳሴ ፡ እንደተነገረ ፡ (ፍት ፡ ነገ ፡ ፲፱ ፡ ፬፻፸፫) ። ሕዝቡን ፡ ያስተናብራቸው ። ረስጠብ ፡ ፰ ። ቀሳውስት ፡ የሚያንሱ ፡ ቢሆን ፡ ጽዋውን ፡ ይያዝ ። በደስ ፡ ፴፩ ። በተፈቀደለት ፡ ጊዜ ፡ ለሕዝቡ ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ያቀርብ ። ረስጣ ፡ ፴፯ ። በምሳ ፡ ጊዜ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወይም ፡ ቄስ ፡ ከዚያ ፡ ባይኖር ፡ በእጁ ፡ አውሎጊያን ፡ (ጸዲቁን) ፡ ይስጥ ።

፪፻፵፱ በደስ ፡ ፴፩ ። ዲያቆን ፡ ያስተምርና ፡ ያጠምቅ ፡ ዘንድ ፡ ወይም ፡ ይቀድስና ፡ ሕዝቡን ፡ ይባርክ ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣን ፡ የለውም ። ከኤጲስቆጶስ ፡ ወይም ፡ ከቄስ ፡ ጋር ፡ ለማገልገል ፡ የተጋ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ የዲቁናውንም ፡ አገልግሎት ፡ ይፈጽም ፡ እንጂ ።

፪፻፶ ረስጣ ፡ ፵፫ ። ሥጋውን ፡ አያቀብል ። እርሱ ፡ ከኤጲስቆጶስ ፡ ወይም ፡ ከቄስ ፡ ይቀበል ፡ እንጂ ። ቍርባኑን ፡ አይሸከም ። ኤጲስቆጶስ ፡ ወይም ፡ ቄስ ፡ ቍርባኑን ፡ በያዘ ፡ ጊዜ ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ለሕዝቡ ፡ ደሙን ፡ ያቀብል ። የካህናት ፡ አገልጋይ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እርሱ ፡ ካህን ፡ አይደለም ። ጼጥ ፡ በእንብሮተ ፡ እድ ፡ አይባርክ ። ለሚበልጠውም ፡ ደሙን ፡ አያቀብል ። ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ለማገልገል ፡ ከእርሱ ፡ የሚያንሱትን ፡

፪፻፶፩ ዘኒቅያ ፡ ፲ወ፯ቱ ፡ ኢይደልምሙ ፡ ለዲያቆናት ፡ ከመ ፡ ይንበሩ ፡ በቅድመ ፡ ቀሳውስት ፡ ወኢበገበዋቲሆሙ ፡ ወኢበውሣጤ ፡ ምሥዋዕ ፡ ወኢበአፍኣ ፡ እምኔሁ ፡ ዘእንበለ ፡ በትእዛዞሙ ።

፪፻፶፪ ዘ፳ወ፩ዱ ፡ ወሊቀ ፡ ዲያቆን ፡ ይቁም ፡ እምድኅረ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በጊዜ ፡ ጸሎት ፡ ወበገቦሁ ፡ ከመ ፡ ዘይንእስ ፡ ወስባኬ ፡ ኵሉ ፡ ጸሎት ፡ ወግብራተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወኵሎ ፡ ዘይከውንሂ ፡ እምዲያቆናት ፡ እለ ፡ ታሕተ ፡ እዴሁ ፡ ተጋእዞ ፡ ወተፋትሖ ፡ ይምትር ፡ ማእከሊሆሙ ፡ ወኢያስርግ ፡ ምንተኒ ፡ እምነ ፡ ውእቱ ፡ ኀበ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ታሕተ ፡ ፍትሑ ፡ ወውእቱ ፡ ሊቀ ፡ ጸሎት ፡ ፍጹም ፡ ወበውስተ ፡ እዴሁ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ግብረ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ኵሉ ፡ ከመ ፡ ኢያፋልስ ፡ ክብረ ፡ ዚአሁ ።

፪፻፶፫ ዘ፳ወ፪ቱ ፡ ወኢይትለዐል ፡ መልዕልቴሁ ፡ ዘእንበለ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ባሕቲቱ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ወኮራ ፡ አቢስቆቢስኒ ፡ ይኩን ፡ በመዓርግ ፡ ከመ ፡ ፪እ ፡ እደዊሁ ፡ ወ፪እ ፡ ክነፊሁ ፡ ለኤጲስቆጶስ ። ወሶበ ፡ የሐውር ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አው ፡ ኀበ ፡ ካልእ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ሲቀ ፡ ዲያቆን ፡ በየማኑ ። ወካልአንሂ ፡ በዐጋሙ ፡ ወውእቱ ፡ ማእከሌሆሙ ፡ ከመ ፡ አብ ፡ ማእከለ ፡ ውሉዱ ። ወኢይደልዎ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ የአዝዝ ፡ ባሕቲቱ ፡ ምንተኒ ፡ እምካህናት ፡ ዘእንበለ ፡ ሲቀ ፡ ዲያቆን ። እስመ ፡ ውእቱ ፡ ሐፃኒ ፡ ሀገር ፡ ወውእቱ ፡ የእምሮሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ወሊቅ ፡ በውስተ ፡ ጸሎት ፡ ውእቱ ፡ ወተመሳሊ ፡ በኵሉ ።

፪፻፶፬ ራብዕ ፡ በእንተ ፡ ተአዝዞቱ ፡ በዲስ ፡ ፴ ፡ ወይሥራዕ ፡ ዲያቆን ፡ ዘይክል ፡ ሠሪዖቶ ፡ ወይንግሮ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ግብራተ ፡ ዐቢያተ ፡ ከመ ፡ ይሥራዕ ፡ ውእቱ ፡ በምክረ ፡ ሕሊናሁ ። ወይኩን ፡ ሊቀ ፡ ዲያቆናት ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ከመ ፡ ዕዝን ፡ ወዓይን ፡ ወአፍ ፡ ወየሀሉ ፡ ምስሌሁ ፡ በ፩ ፡ ልብ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ዘኢያስተሐምም ፡ ዘእንበለ ፡ ግብራት ፡ ዐቢያን ፡ በከመ ፡ አምከሮ ፡ ዮቶር ፡ ሐሙሁ ፡ ለሙሴ ፡ በእንተ ፡ ሠሪዐ ፡ ፍትሕ ፡ ማእከለ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ወተወክፈ ፡ ምክረ ፡ ዚአሁ ፡ ወአሠነየ ፡ ደኃሪታ ።

ይዘዝ ፡ እንጂ ።

፪፻፶፩ ኒቅያ ፡ ፲፯ ። ዲያቆናት ፡ በቀሳውስት ፡ ፊት ፡ ባጠገባቸውም ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ ከርሱም ፡ ውጭ ፡ ቢሆን ፡ አይቀመጡ ፡ በነርሱ ፡ ትእዛዝ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ።

፪፻፶፪ ሊቀ ፡ ዲያቆን ፡ በጸሎት ፡ ጊዜ ፡ ከኤጲስቆጶስ ፡ በኋላ ፡ በእጠገቡ ፡ ይቁም ። ትንሽ ፡ እንደመሆኑ ፡ የጸሎት ፡ ሁሉና ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሥራዎች ፡ ሰባኪ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ። ከሥልጣኑ ፡ በታች ፡ ካሉ ፡ ዲያቆናት ፡ የሚሆነውንም ፡ ጠብ ፡ ክርክር ፡ ይወስን ። ከርሱ ፡ ወደ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ምንም ፡ አይውሰድ ። እነርሱ ፡ ከሥልጣኑ ፡ በታች ፡ ናቸውና ። ፍጹም ፡ የጸሎት ፡ አለቃ ፡ ነው ። መዓርጉን ፡ እንዳያዋርድ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ በእጁ ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ።

፪፻፶፫ ፳፪ ። ከኤጲስቆጶስ ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ በበላዩ ፡ ከፍ ፡ አይበል፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ነውና ። ምክትል ፡ ኤጲስቆጶስም ፡ በመዓርግ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ እንደ ፡ ሁለት ፡ እጆቹና ፡ እንደ ፡ ሁለት ፡ ክንፎቹ ፡ ይሁን ። ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ ሊቀ ፡ ዲያቆን በቀኙ ፡ ሌሎቹም ፡ በግራው ፡ ሊሆኑ ፡ ይገባል ። እርሱ ፡ በነርሱ ፡ መካከል ፡ ነው ። አባት ፡ በልጆቹ ፡ መካከል ፡ እንደሆነ ። ኤጲስቆጶስ ፡ ከሊቀ ዲያቆን ፡ በቀር ፡ ከካህናት ፡ ወገን ፡ ብቻውን ፡ ሊያገዝ ፡ አይገባውም ፡ አገር ፡ አሳዳሪ ፡ ነውና፡ እርሱም ፡ ሕዝቡን ፡ ያውቃቸዋል ። በጸሎት ፡ ጊዜ ፡ አለቃ ፡ ነው ። በሁሉም ፡ የሚመስል ፡ ነው ።

፪፻፶፬ ፬ተኛ ፡ ስለ ፡ መታዘዙ ፡ ይናገራል ። በዲስ ፡ ፴ ። ዲያቆን ፡ ሊሠራ ፡ የሚችለውን ፡ ይሥራ ። በርሱ ፡ ፈቃድ ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ታላላቆቹን ፡ ሥራዎች ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ይንገረው ። ሊቀ ፡ ዲያቆናት ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ እንደ ፡ ጆሮና ፡ እንደ ዓይን ፡ እንደ ፡ አፍም ፡ ይሁነው ። በአንድ ፡ ልብ ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ይኑር ፡ ከታላቆቹ ፡ ሥራዎች ፡ በቀር ፡ የማይጨነቅ ፡ እንዲሆን ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ፍርድን ፡ ለማከናወን፡ አማቱ ፡ ዮቶር ፡ ሙሴን ፡ እንዳማከረው ፡ እርሱም ፡ ምክሩን ፡ ተቀብሎ ፡ ፍጻሜዋን ፡ አሳመረ ።

### አንቀጽ ፡ ፯ ።

፪፻፶፭ ሥርዋጽ ፡ ውስተ ፡ ፩ ፡ እመጻሕፍተ ፡ ሮም ፡ ዘ፳ወ፯ ፡ ወኢይቅንቱ ፡ ሐቌሆሙ ፡ ዲያቆናት ፡ በዝናር ፡ በጊዜ ፡ ጸሎት ፤ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ግዑዛን ፡ ወኢይቀንዮሙ ፡ ዘእንበለ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ንጉሠ ፡ ኵሉ ፡ ወአምላከ ፡ ኵሉ ። ወክብሮሙ ፡ ለዲያቆናት ፡ ይትዓወቅ ፡ በዝንቱ ፡ እምካልአኒሆሙ ፤ ወዝንቱ ፡ አንቀጽ ፡ ዘእንበለ ፡ ግዘት ።

፪፻፶፮ ዘ፴ወ፬ቱ ፡ ወይደልወክሙ ፡ አ ፡ ዲያቆናት ፡ ክመ ፡ ተሐውጽዎሙ ፡ ለጽኑሳን ፡ ወትንግርዎሙ ፡ ለኤጲስቆጶሳቲክሙ ፡ ግብረ ፡ ተጽናሶሙ ፡ ለጽኑሳን ፤ እስመ ፡ ለክሙ ፡ ይደልወክሙ ፡ ክመ ፡ ትኩኑ ፡ ሎቱ ፡ ነፍስ ፡ ወሥጋ ፡ በኵሉ ፡ ግብር ፡ ወትትአዘዙ ፡ ሎቱ ፡ ወትፈጽሙ ፡ ትእዛዛቲሁ ፡ ክመ ፡ አብ ፡ ወመኰንን ፡ ወመምህር ።

፪፻፶፯ በደስ ፡ ፺ቱ ፡ ወእመ ፡ ወሀበ ፡ ዲያቆን ፡ ለ፩ሂ ፡ ንዋየ ፡ በእንተ ፡ ክዊኖቱ ፡ ጽኑስ ፡ ወኀብእ ፡ እምኤጲስቆጶስ ፡ ወአበተዋደይዎ ፡ ኀበ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወናሁ ፡ ረሰይዎ ፡ ፅሩዐ ፡ እምነ ፡ ጽኑሳን ፡ ወይትሀወኩ ፡ ሕዝብ ፡ በእንጕርጕሮ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወአኮ ፡ ላዕሌሁ ፡ ባሕቲቱ ፤ አላ ፡ ላዕለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይሰምዕ ፡ በውእቱ ፡ ወበውእቶሙ ፡ በከመ ፡ ሰምዐ ፡ በአሮን ፡ ወበእኅቱ ፡ ኀበ ፡ ተናገረ ፡ በእንተ ፡ ሙሴ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ለምንት ፡ ኢፈራህክሙ ፡ ሐምዮቶ ፡ ለሙሴ ፡ ቍልዔየ ።

፪፻፶፰ ረስጣ ፡ ፲ወ፰ቱ ፡ ወይኩኑ ፡ ዲያቆናት ፡ ገባርያነ ፡ ግብር ፡ ሠናይ ፡ በሌሊት ፡ ወበመዓልት ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ መካን ፤ ዘሰ ፡ ይትለአክ ፡ ሠናየ ፡ ዘእንበለ ፡ ኃጢአት ፡ ውእቱ ፡ ይረብኅ ፡ ወይነሥእ ፡ መክፈልተ ፡ ሠናየ ።

፪፻፶፱ ኃምስ ፡ ምክንያት ፡ ዘያወድቆ ፡ እመዓርገ ፡ መልእክት ፡ እሐዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘተነግረ ፡ በእንቀጸ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወቀሲስ ፡ ለዙሉ ፡ ወውእቱ ፡ ዘይመትር ፡ ኵሎ ፡ ዲያቆናተ ፡ ዘአጥረየ ፡ ዘንተ ፡ መዓርገ ፡ በሕልያን ፡ አው ፡ በኀይል ፡ አው ፡ በትምይንት ፡ አው ፡ በአስፍዎ ፡ ክመ ፡ የሀብ ፡ ሕልያነ ፡ አው ፡ በነሢአ ፡ ሢመት ፡ ፪ተ ፡ ጊዜ ፡ እው ፡ ዘአውሰበ ፡ ፪ተ ፡ አንስተ ፡ አው ፡ ዘያዘልፍ ፡ ስካረ ፡ ወይትጌበር ፡ እከያተ ፡ ወይነብር ፡ በኀዲገ ፡ ገቢረ ፡ ሠናይ ። እው ፡ ዘነሠሠ ፡

### ስለ ፡ ዲያቆናት ።

፪፻፶፭ ሥርዋጽ ። ከሮም ፡ መጽሐፍ ፡ በአንዱ ፡ ውስጥ ፡ በ፳፯ኛው ፡ አንቀጽ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ። በጸሎት ጊዜ ፡ ዲያቆናት ፡ ወገባቸውን ፡ በዝናር ፡ አይታጠቁ ፤ እነርሱ ፡ ነጻ ፡ ናቸውና ። የሁሉ ፡ ንጉሥና ፡ የሁሉ ፡ አምላክ ፡ ከሚሆን ፡ ከጌታችን ፡ ከኢየሱስ ፡ በቀር ፡ የሚገዛቸው ፡ የለም ። የዲያቆናት ፡ ከብራቸው ፡ ከሌሎቹ ፡ በዚህ ፡ ይታወቃል ። ይህም ፡ ያልተወገዘበት ፡ አንቀጽ ፡ ነው ።

፪፻፶፮ ፴፬ ። ዲያቆናት ፡ ሆይ ፡ የተቸገሩትን ፡ ልትጐበኙዋቸው ፤ የተቸገሩትንም ፡ የችግራቸውን ፡ ግዳጅ ፡ ለኤጲስቆጶሶቻችሁ ፡ ልትነግሩዋቸው ፡ ይገባችኋል ። በሥራው ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ነፍስና ፡ እንደ ፡ ሥጋ ፡ ትሆኑለት ፡ ዘንድ ፡ ትታዘዙለት ፡ ዘንድ ፡ ትእዛዙንም ፡ ትፈጽሙለት ፡ ዘንድ ፡ ይገባችኋልና ። አባት ፡ ገዥ ፡ መምህር ፡ እንደ መሆኑ ፡ መጠን ።

፪፻፶፯ በደስ ፡ ፺ ። ዲያቆን ፡ ለአንዱ ፡ ስለ ፡ ችግሩ ፡ ገንዘብ ፡ ቢሰጥ ፤ ይህንኑም ፡ ከኤጲስቆጶሱ ፡ ቢሸሽግ ፡ ከኤጲስቆጶሱ ፡ ዘንድ ፡ ቢከሱት ፡ እነሆ ፡ ከችግረኞቹ ፡ ይልቅ ፡ ችግረኛ ፡ አደረጉት ። ሕዝቡ ፡ በማንጐራጐር ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ይታወካሉ ። በርሱ ፡ ብቻ ፡ የሚታወኩ ፡ አይደለም ። በእግዚአብሔርም ፡ ላይ ፡ ነው ፡ እንጂ ። በርሱና ፡ በነርሱ ፡ መካከል ፡ ይሰማል ። ወዳጄን ፡ ሙሴን ፡ ስታሙት ፡ ለምን ፡ አልፈራችሁም ፡ ሲል ፡ በተናገረበት ፡ ጊዜ ፡ በአሮንና ፡ በእኅቱ ፡ እንደ ፡ ሰማ ፡ ( ዘኍ ፡ ፲፪ ፡ ፪-፯) ።

፪፻፶፰ ረስጣ ፡ ፲፰ ። ዲያቆናት ፡ መልካም ፡ ሥራን ፡ በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ በቦታው ፡ ሁሉ ፡ የሚሠሩ ፡ ይሁኑ ። ያለ ፡ ኃጢአት ፡ በጎ ፡ ማገልገልን ፡ ያገለገለ ፡ ይህ ፡ ይጠቀማል ፡ በጎ ፡ ድርሻንም ፡ ይቀበላል ።

፪፻፶፱ ፭ኛ ፡ ከእገልግሎት ፡ መዓርግ ፡ የሚያሽረውን ፡ ምክንያት ፡ ይናገራል ። ከነርሱ ፡ አንዱ ፡ ለሁሉ በአንቀጸ ፡ ኤጲስቆጶሳትና ፡ በአንቀጸ ፡ ቀሳውስት ፡ የተነገረ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ዲያቆናትን ፡ የሚሽር ፡ ነው ። በመማለጃ ፡ ይሆን ፡ መዓርግ ፡ ገንዘብ ፡ ያደረገ ፡ ወይም ፡ በኀይል ፡ በተንኰል ፡ መማለጃን ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ ተስፋ ፡ የሰጠ ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ሹመትን ፡ የተቀበለ ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡ ሚስት ፡ ያገባ ፡ ወይም ፡ ዘወትር ፡ የሚሰክርና ፡ በጎውን ፡ ሥራ ፡ ትቶ ፡ ክፉ

እምዘይሌቅሕ ፡ ርዴ ፡ እው ፡ ዘይከውን ፡ ስምዐ ፡ በሐሰት ፡ እው ፡ ዘየሐሚ ፡ እው ፡ ዘይገብር ፡ ትዕቢተ ፡ እው ፡ ዘይሰክብ ፡ ምለለ ፡ ዘማዊት ፡ ብእሲት ፡ እው ፡ ዘሖረ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ዘእን በለ ፡ ትእዛዘ ፡ ሊቁ ፡ እው ፡ ዘዘበጠ ፡ ፩ደሂ ፡ ለአፍርሆተ ፡ ሰብእ ፡ እው ፡ ተወከፈ ፡ ጥምቀተ ፡ እምዕልዋን ፡ እው ፡ ቀረበ ፡ እምቍርባኖሙ ፡ እው ፡ ጸለየ ፡ ምስሌሆሙ ፡ እው ፡ ዘይ·ኀረ ፡ ብእ ሲቶ ፡ በእንተ ፡ ምክንያተ ፡ ተልእኮ ፡ ለእግዚአ ብሔር ፡ እው ፡ በእንተ ፡ ምንዙስና ፡ ወጽሙና ፡ እው ፡ ዘተሥዕረ ፡ በርትዕ ፡ ወእምዝ ፡ ተኀበለ ፡ ላዕለ ፡ መልእክቱ ፡ እው ፡ ዘአስተሐቀሮ ፡ ለኤ ጲስቆጶስ ፡ ዘዚእሁ ፡ ወተፈልጠ ፡ እምኔ ፡ ምሥ ዋዑ ፡ ወገብረ ፡ ምሥዋዐ ፡ ባሕቲቱ ፡ ሶበኒ ፡ ጸውዖ ፡ ወኢተለጥዎ ፡ እው ፡ ዘፈለሰ ፡ እም ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ኀበ ፡ ካልእ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ ያን ፡ ወእምዝ ፡ ገብአ ፡ ኀቤሃ ፡ እው ፡ ሖረ ፡ ኀበ ፡ ነጊድ ፡ እው ፡ ኀበ ፡ ምንዙስና ፡ ዘእንበለ ፡ መባሕተ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወመልእክቱ ፡ ፈድ ፋደሰ ፡ ለእመ ፡ ሖረ ፡ እንዘ ፡ ውጉዝ ፡ ውእቱ ፡ እው ፡ ዘአብእ ፡ ብእሲተ ፡ ትክተ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እው ፡ ዘይሜጥዋ ፡ ቍርባነ ፡ እው ፡ ዘይገብር ፡ ተክሊለ ፡ ፩ዱሂ ፡ በጽሚት ።

፪፻፷ ወዝንቱ ፡ ውዑእ ፡ እምዘተነግረ ፡ በአንቀጸ ፡ ካህናት ፡ ወእምኔሁ ፡ ዘተነግረ ፡ በዝንቱ ፡ አን ቀጽ ፡ ወውእቶሙ ፡ ፪ቱ ፡ ግብራት ፡ ፩ዱ ፡ እም ኔሆሙ ፡ እንቆራ ፡ ፱ቱ ፡ እመ ፡ ተካየዱ ፡ ላዕለ ፡ ነፍሶሙ ፡ በጊዜ ፡ ሢመቶሙ ፡ ከመ ፡ ውእቶሙ ይንበሩ ፡ እንበለ ፡ ብእሲት ፡ ወእምዝ ፡ እው ሰቡ ፡ እምድኅረ ፡ ሢመቶሙ ፡ ይትመተሩ ፡ እምሢመተ ፡ ዲቁና ።

፪፻፷፩ ወዳግምኒ ፡ ዘኒቅያ ፡ ፲ወ፩ዱ ፡ ቀጠጅ ፡ ፲ቱ ፡ ሶበ ፡ ተአመነ ፡ ዲያቆን ፡ እምድኅረ ፡ ሢመቱ ፡ ኀጢአቶ ፡ ዘገብረ ፡ ቀዲሙ ፡ ይሰደድ ፡ ወኢይ ባእ ፡ ውስተ ፡ መልእክተ ፡ ቅዳሴ ። ለእመሰ ፡ ነገረ ፡ ባቲ ፡ ወገሠጽዎ ፡ ገሃደ ፡ በውስተ ፡ ጉባኤ ፡ ይንበር በመዓርገ ፡ ንፍቀ ፡ ዲያቆን ።



ትን ፡ የሚያደርግ ፡ ወይም ፡ ካበደረው ፡ ትር ፍን ፡ የሚፈልግ ፡ ወይም ፡ በሐሰት ፡ የሚመሰ ክር ፡ ወይም ፡ የሚያማ ፡ ትዕቢትን ፡ የሚያደ ርግ ፡ ወይም ፡ ከዘማዊቱ ፡ ጋር ፡ የሚተኛ ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ እለቃው ፡ ትእዛዝ ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ የሚሄድ ፡ ወይም ፡ ሰውን ፡ ለማስፈራራት ፡ አን ድን ፡ ስንኳ ፡ የሚማታ ፡ ወይም ፡ ከመናፍቃን ፡ ዘንድ ፡ ጥምቀትን ፡ የተቀበለ ፡ ወይም ፡ ከቍር ባናቸው ፡ የቈረበ ፡ ወይም ፡ ከነርሱ ፡ ጋር ፡ የጸ ለየ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በማገልገል ፡ ምክንያት ፡ ወይም ፡ በምንኵስናና ፡ በተባሕትዎ ፡ ምክን ያት ፡ ሚስቱን ፡ የፈታ ፡ ወይም ፡ በሚገባ ፡ የተ ሻረ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በአገልግሎቱ ፡ ላይ ፡ የተደፋፈረ ፡ ወይም ፡ የራሱን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ የአስተሐቀረ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያኑም ፡ ተለ ይቶ ፡ ብቻውን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሠራ ፡ በጠራውም ፡ ጊዜ ፡ ባይመጣ ፡ ወይም ፡ ከርሱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወደ ፡ ሌላይቱ ፡ ቤተ ፡ ክርስ ቲያን ፡ የተሰደደ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደርስዋ ፡ ቢመለስ ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ ፈቃድ ፡ መንገድ ፡ የሄደ ፡ ወይም ፡ የመነኵሰ ፡ ይልቁ ንም ፡ ተወግዞ ፡ ሳለ ፡ ቢሄድ ፡ ወይም ፡ ከማ ዳጅዋ ፡ (ከደሟ) ፡ ያልነጸችውን ፡ ሴት ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያገባ ፡ ወይም ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ የሚያቀብላት ፡ ወይም ፡ ለአንዱስ ፡ እንኳ ፡ ተክሊልን ፡ በስውር ፡ የሚያደርግ ፡ ይሻር ።

፪፻፷ ይህ ፡ በአንቀጸ ፡ ካህናት ፡ ከተነገረው ፡ የወጣ ፡ ነው ። (ፍት ፡ ነ ፡ ፱ ፡ ፳፱) ። ከርሱም ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ የተነገረ ፡ ነው ። እነዚህም ፡ ሁለት ፡ ክፍሎች ፡ ናቸው ። ከነርሱ ፡ አንዱ ፡ እንቆራ ፡ ፱ ። በተሾሙ ፡ ጊዜ ፡ ያለ ፡ ሴት ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ቢሳሉ ፡ ከተሾሙም ፡ በኋላ ፡ ቢያገቡ ፡ ከዲ ቁና ፡ ሹመት ፡ ይሻሩ ።

፪፻፷፩ ፪ኛ ፡ ኒቅያ ፡ ፲፩ ፡ ቀጠጅ ፡ ፲ ። ዲያቆን ፡ ከተ ሾመ ፡ በኋላ ፡ ቀድሞ ፡ የሠራውን ፡ ኃጢአቱን ፡ ቢያምን ፡ ይለይ ፡ በቅዳሴም ፡ ጊዜ ፡ ለማገልገል አይግባ ። ነገር ፡ ግን ፡ እርሷን ፡ ቢናገር ፡ በአደ ባባይም ፡ በግልጽ ፡ ቢረቱት ፡ በንፍቀ ፡ ዲቁና ፡ መዓርግ ፡ ይኑር ።

# አንቀጽ ፡ ሳምን ።

በእንተ ፡ ንፍቀ ፡ ዲያቆን ፡ ወአናጕንስጢስ ፡ ወአንባቢ ፡ ወዐጻዊ ፡ ወመዘምር ፡ ወዲያቆናዊት ።

፪፻፷፪ ወውእቱ ፡ ፰ቱ ፡ አክፋል ፡ ቀዳማዊ ፡ በእንተ ፡ ሥርዓታት ፡ ድልዋት ፡ ይቤሉ ፡ ሐዋርያት ፡ ረስጣ ፡ ፲ወ፰ቱ ፡ ይሠየም ፡ አናጕንስጢስ ፡ እምድኅረ ፡ ፈተንዎ ፡ ቅድመ ፡ ኢይኩን ፡ አብዛኄ ፡ ነገር ፡ ወኢስካሬ ፡ ወኢዘይነብብ ፡ ስላቀ ፡ ወይኩን ፡ ሎቱ ፡ ሑረት ፡ ሠናይ ፡ ወመፍቀሬ ፡ ሠናያት ፡ ወዘያፈጥን ፡ ሐዊረ ፡ ኀበ ፡ ጉባኤ ፡ እንተ ፡ በውስቴታ ፡ ይዜክሩ ፡ ግብረ ፡ መለኮት ፡ ወይኩን ፡ ተአዛዜ ፡ ወዘያሤኒ ፡ አንብቦ ፡ ወየአምር ፡ ገጸ ፡ ምንባብ ፡ ወይተግህ ፡ ለገቢሮቱ ። ወያአምር ፡ ከመ ፡ ይደልዎ ፡ ለአንባቢ ፡ ይግበር ፡ ዘያነብቦ ፡ ወዘይመልእ ፡ በአዕዛነ ፡ ስማዕያን ፡ በዘይደሉ ፡ ሎቱ ፡ ወየአምር ፡ ባህለ ፡ ቃሉ ። ወለዘኒ ፡ ይመልእ ፡ በአዕዛነ ፡ ካልአን ፡ መፍትው ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ያእምር ፡ ወይለቡ ፡ ዘያነብብ ፡ እኮኑ ፡ ይጸሐፍ ፡ ዝንቱ ፡ ከዊነ ፡ ኃጢአት ፡ ሎቱ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ።

፪፻፷፫ ወይቤ ፡ ጳውሎስ ፡ ጤት ፡ ፬ቱ ፡ እምድኅረ ፡ ጸሐፈ ፡ ሥርዓተ ፡ ዲያቆናት ፡ ወከማሁ ፡ አንስትኒ ፡ ካዕበ ፡ ይኩና ፡ ንጹሓተ ፡ ወንቁሓተ ፡ በሕሊናሆን ፡ ወዘይትአመንዎን ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ግብር ፡ ወኢይኩና ፡ መስተዳጕጻተ ። ዘ፲ወ፰ ፡ ወለእመ ፡ ተኀረ ፡ ዕቤረ ፡ ኅረይ ፡ ዘኢየሐጽጽ ፡ መዋዕሊሃ ፡ እምስሳ ፡ ዓም ፡ ወእንተ ፡ ተወሰበት ፡ ለአሐዱ ፡ ብእሲ ፡ ወዘሰምዐ ፡ ይከውኑ ፡ ላቲ ፡ በምግባር ፡ ሠናይ ፡ ወዘአልኀቀት ፡ ውሉዳ ፡ ወተወከፈት ፡ ነግደ ፡ ወሐፀበት ፡ እግረ ፡ ቅዱሳን ፡ ወተራኅርኀት ፡ ላዕለ ፡ ጽዑቃን ፡ ወሖረት ፡ በኵሉ ፡ ምግባረ ፡ ሠናይ ።

፪፻፷፬ ድስቅ ፡ ፲ወ፯ቱ ፡ ወይኅረይ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አንስተ ፡ ቅዱሳተ ፡ ወይሢሞን ፡ ዲያቆናውያተ ፡ ለተልእኮ ፡ አንስት ፡ እስመ ፡ ኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይፈኑ ፡ ዲያቆነ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ አንስት ፡ በእንተ ፡ መፍቅደ ፡ ጽዋዔሆን ፡ ዘእንበለ ፡ ዲያቆናዊት ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ። ወዓዲ ፡ በእንተ ፡ ብእሲት ፡



# አንቀጽ ፡ ፰ ።

ስለ ፡ ንፍቀ ፡ ዲያቆን ፡ ስለ ፡ አናጕንስጢስና ፡ ስለ ፡ አንባቢ ፡ ስለ ፡ በረኛውና ፡ ስለ ፡ መዘምር ፡ ስለ ፡ ዲያቆናዊትም ፡ ይናገራል ።

፪፻፷፪ ይኸውም ፡ ፰ ፡ ክፍል ፡ ነው ። መጀመሪያው ፡ ስለሚገቡ ፡ ውሳኔዎች ፡ ሐዋርያት ፡ እንዲህ ፡ አሉ ። ረስጣ ፡ ፲፰ ፡ አናጕናስጢስ ፡ አስቀድሞ ፡ ከፈተኑት ፡ በኋላ ፡ ይሾም ። ነገር ፡ የሚያበዛ ፡ አይሁን ። ስካራም ፡ ዘበትንም ፡ የሚናገር ፡ አይሁን ። በጎ ፡ አኗኗር ፡ ያለው ፡ በጎንም ፡ የሚወድ ፡ ነገረ ፡ መለኮት ፡ ወደሚነገርበት ፡ ጉባኤ ፡ የሚፋጠን ፡ ይሁን ። ታዛዥ ፡ አከናውኖ ፡ የሚያነብ ፡ የንባብ ፡ ስልት ፡ የሚያውቅ ፡ ለመሥራት ፡ የሚተጋ ፡ ይሁን ። አንባቢ ፡ የሚያነበውን ፡ መሥራት ፡ እንዲገባውና ፡ ስርሱም ፡ በሚገባ ፡ ገንዘብ ፡ በሰሚዎች ፡ ጆሮ ፡ የሚያስረዳውን ፡ መሥራት ፡ እንዲገባው ፡ ይወቅ ። ኀይለ ፡ ቃሉን ፡ ይወቀው ፡ በሌሎቹ ፡ ጆሮ ፡ የሚያስረዳውንም ፡ የሚያነበው ፡ ሰው ፡ ሊያውቀውና ፡ ሊያስተውለው ፡ ይገባል ። ይህን ፡ አለማወቁ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ኃጢአት ፡ ሆኖ ፡ ይቆጠርበታልና ።

፪፻፷፫ ጳውሎስም ፡ ጤት ፡ ፬ ፡ የዲያቆናትን ፡ ሥርዓት ፡ ከጻፈ ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ አለ ። እንዲሁም ፡ ሴቶች ፡ በአሳባቸው ፡ ንጹሖችና ፡ ንቁሖች ፡ በሥራውም ፡ ሁሉ ፡ የሚያምኑዋቸው ፡ ይሁኑ ። ነገር ፡ አዋሳጆችም ፡ አይሁኑ ። ፲፰ ፡ ዲያቆናዊትን ፡ ልትሾም ፡ ብትመርጥ ፡ ዕድሜዋ ፡ ከስሳ ፡ ዓመት ፡ ያላነሰውን ፡ አንድ ፡ ወንድ ፡ ያገባችውን ፡ በበጎ ፡ ሥራ ፡ ምስክር ፡ የሆኑላትን ፡ ልጆቿን ፡ ያሳደገችውን ፡ እንግዳ ፡ የምትቀበለውን ፡ የቅዱሳንን ፡ (የመነኮሳቶቹን) ፡ እግር ፡ የምታጥበውን ፡ ለተጨነቁት ፡ የምትራራውን ፡ በበጎ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ የኖረችውን ፡ ሹማት ።

፪፻፷፬ ድስቅ ፡ ፲፯ ። ኤጲስቆጶስ ፡ ንጹሖቹን ፡ ሴቶች ፡ መርጦ ፡ ሴቶችን ፡ ለማገልገል ፡ ዲቁናን ፡ ይሹማቸው ። ሴቶች ፡ ስለሚያሻቸው ፡ ነገር ፡ በጠና ፡ ጊዜ ፡ ከዲያቆናዊቱ ፡ በቀር ፡ ዲያቆንን ፡ ወደ ፡ ሴቶች ፡ ቤት ፡ ሊልክ ፡ አይገባምና ። ስለዚህና ፡ ዳግመኛም ፡ ስለማያጠምቋት ፡ ሴት ፡

ዘያጠምቅዋ ፡ ከመ ፡ ትቅባእ ፡ እመሊያልዩሃ ፡ ወእምድኅረዝ ፡ ይቅባእ ፡ ዲያቆን ፡ ፍጽማ ፡ አምዘያት ፡ ቅዱስ ፡ እስመ ፡ ኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኅጽር ፡ ብእሲ ፡ ብእሲተ ፡ ዕርቅተ ፡ ወኢይግሥሥዋን ፡ ዘእንበለ በአንብሮ ፡ እድ ፡ ባሕቲቱ ።

፪፻፳፭ ዳግም ፡ ክፍል ፡ በእንቲ ፡ ሢመቲ ፡ ረስጣ ፡ ፳ወ፩ቱ ፡ በደስ ፡ ፯ቱ ፡ በስ ፡ ፵ወ፰ቱ ፡ አናጕንስጢስ ፡ በጊዜ ፡ ይሠየም ፡ የሀቦ ፡ ሎቱ ፡ ኤጲስ ቆጶስ ፡ መጽሐፈ ፡ ወንጌል ፡ ቅድመ ፡ ወኢየንብር ፡ እደ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወኢላዕለ ፡ ንፍቀ ፡ ዲያቆን ፡ ኢያንብር ፡ እደ ፡ አላ ፡ ይግበር ፡ ሎሙ ፡ ስመ ፡ ከመ ፡ ይትልውዎሙ ፡ ለዲያቆናት ። ወለ አመ ፡ ኮነ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ብእሲት ፡ ኢይሠየም ፡ ዘእንበለ ፡ እመ ፡ ኢኮንዎ ፡ ስምዐ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ርኑቅ ፡ ውእቱ ፡ አምአንስት ። ወለመዘምራንሂ ካዕበ ፡ ይባርኮሙ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወኢያንብር ፡ እደ ፡ ላዕለ ፡ ድንግል ፡ አላ ፡ ምሥጢራ ፡ ባሕቲታ ፡ እንተ ፡ ትረስያ ፡ ድንግለ ።

፪፻፳፮ ሣልስ ፡ ክፍል ፡ በእንተ ፡ ሥርዐቶሙ ፡ ድስቅ ፡ ቀዳማዊ ፡ ንፍቀ ፡ ዲያቆናትስ ፡ ከመ ፡ እንተ ፡ ረዳእያን ፡ አናጕንስጢስ ፡ አንባቢ ፡ እለ ፡ አብስሊድስ ፡ መዘምራን ። ዘ፲ወ፪ቱ ፡ ወይቁም ፡ አናጕንስጢስ ፡ ውስተ ፡ ማእከል ፡ ላዕለ ፡ መካን ፡ ልዑል ፡ ወያንብብ ፡ እመጻሕፍተ ፡ ብሊት ፡ እምነቢሉ ፡ መጻሕፍት ፡ በበ፪ቱ ፡ ክፍል ፡ ወይዘምሩ ፡ ካል አኒሆሙ ፡ እመዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ ወይቁሙ ፡ በጸውተ ፡ ኆዋኅውኒ ፡ ካዕበ ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ ምብዋእሙ ፡ ለእደው ፡ ወይዕቀብዋ ።

፪፻፳፯ ጸከ ፡ ፵ወ፭ቱ ፡ ፵ወ፮ቱ ፡ ፵ወ፯ቱ ፡ ዘ፳ወ፯ቱ ፡ ዶቅ ፡ ፳ወ፩ዱ ፡ ፳ወ፪ቱ ፡ ፳ወ፲ቱ ፡ ፵ወ፲ቱ ፡ ኢይደልዎሙ ፡ ለንፍቀ ፡ ዲያቆናት ፡ ከመ ፡ ይትለአኩ ፡ በመካነ ፡ ዲያቆናት ፡ ወኢከመ ፡ ይግሥሡ ፡ ንዋየ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢይደልዎ ፡ ለንፍቀ ፡ ዲያቆን ፡ ከመ ፡ ይልበስ ፡ ሞጣሕተ ፡ እው ፡ ይትፈለጥ ፡ እምአንቀጽ ። ወኢ ፡ ለአናጕንስጢሳውያን ፡ ወኢ ፡ ለመዘምራን ፡ ከመ ፡ ይልበሱ ፡ ሞጣሕተ ፡ ሶበ ፡ ያንብቡ ፡ ወኢለዐቀብት ፡ ከመ ፡ ይትፈለጡ ፡ እምአንቀጽ ፡ እሑተ ፡ ሰዓተ ። ጸከ ፡ ዘ፵ወ፲ቱ ፡ ወኢለዐቀብት ፡ ከመ ፡ ይትፈለጡ ፡ እምአንቀጽ ፡ እመኒ ፡ እሑተ ፡ ሰዓተ ።



ሰውነቷን ፡ ሜሮን ፡ ትቀባ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዲያቆን ፡ ፊትዋን ፡ ሜሮን ፡ ይቀባት ። ወንድ ፡ የተራቆተችውን ፡ ሴት ፡ ማየት ፡ አይገባውምና ። በቃል ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ በእን ብሮተ ፡ እድ ፡ አይሾሚቸው ።

፪፻፳፭ ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ስለ ፡ ሹመቱ ፡ ይናገራል ። ረስጣ ፡ ፳፯ ፡ በደስ ፡ ፯ ። በስ ፡ ፵፰ ። አናጕንስ ጢስ ፡ በተሾመ ፡ ጊዜ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አስቀ ድሞ ፡ የወንጌልን ፡ መጽሐፍ ፡ ይስጠው ። በር ሱ ፡ ላይ ፡ አንብሮተ ፡ እድ ፡ አያድርግ ። በን ፍቀ ፡ ዲያቆኑም ፡ ላይ ፡ አንብሮተ ፡ እድ ፡ አያድርግ ። ዲያቆናትን ፡ ያገለግሉ ፡ ዘንድ ፡ ስም ያውጣላቸው ፡ እንጂ ። ከሴት ፡ የራቀ ፡ አንደ ሆነ ፡ ካልመሰከሩለት ፡ በቀር ፡ ሚስት ፡ የሌ ለቸው ፡ ቢሆን ፡ አይሾም ። መዘምራኑንም ፡ ዳግመኛ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ይባርካቸው ። በድንግ ሊቱ ፡ ላይ ፡ አንብሮተ ፡ እድ ፡ አያድርግ ። ድንግል ፡ የምታደርጋት ፡ ሥራዋ ፡ ብቻ ፡ ናት ፡ እንጂ ።

፪፻፳፮ ሦስተኛው ፡ ክፍል ፡ ስለ ፡ ሥርዓታቸው ፡ ይናገ ራል ። ድስቅ ። መጀመሪያው ፡ ንፍቀ ፡ ዲያቆ ናት ፡ ረዳቶች ፡ አናጕንስጢስ ፡ አንባቢ ፡ እልአ ብስሊድስ ፡ መዘምራን ፡ መሆናቸውን ፡ ይናገ ራል ። ፲፪ ። ንፍቀ ፡ ዲያቆን ፡ ከፍ ፡ ካለ ፡ ቦታ ፡ መካከል ፡ ቁሞ ፡ ከብሉይ ፡ ኪዳን ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ ክፍል ፡ ያንብብ ። ሌሎችም ፡ ከዳዊት ፡ መዝሙር ፡ ይድገሙ ። ዳግመኛም ፡ በረኞቹ ፡ በወንዶቹ ፡ በር ፡ መግቢያ ፡ ቁመው ፡ ይጠብቁ ።

፪፻፳፯ ጸከ ፡ ፵፭ ። ፵፮ ። ፵፯ ፡ ፳፯ ። ዶቅ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪ ። ፳፲ ። ፵፲ ። ንፍቀ ፡ ዲያቆናት ፡ በዲያቆናት ፡ ማዕርግ ፡ ማገልገል ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳት ፡ መንካት ፡ አይገባቸውም ። ንፍቀ ፡ ዲያቆን ፡ የሞጣሕት ፡ ልብስ ፡ መል በስ ፡ አይገባውም ። ወይም ፡ ከበሩ ፡ መለየት ፡ አይገባውም ። አናጕስጢሳውያንና ፡ መዘም ራንም ፡ በሚያነቡበት ፡ ጊዜ ፡ ሞጣሕት ፡ ይለ ብሱ ፡ ዘንድ ፡ ጠባቂዎችም ፡ ከበሩ ፡ አንዲት ፡ ሰዓት ፡ እንኳ ፡ ይለዩ ፡ ዘንድ ፡ አይገባቸውም ። ጸከ ፡ ፵፲ ። ጠባቂዎችም ፡ ከበሩ ፡ አንዲት ፡ ሰዓ ትም ፡ ቢሆን ፡ መለየት ፡ አይገባቸውም ።

አንቀጽ ፡ ፮ ።

፪፻፸፰ ጸኑ ፡ ፴ወ፱ቱ ፡ ኢይደልዎሙ ፡ ለአርድእት ፡ ወኢለዐቀብት ፡ ከመ ፡ ይመጥዉ ፡ ጽዋዐ ፡ ቍር ባን ።

፪፻፸፱ ረስጣ ፡ ፵ወ፱ቱ ፡ ወዲያቆናውያት ፡ አንስት ፡ ኢይባርካ ፡ ወኢይግበራ ፡ ምንተኒ ፡ እምዘ ይገብርዎ ፡ ቀሳውስት ፡ ወዲያቆናት ፡ አላ ፡ ይዕ ቀባ ፡ አንቀጸ ፡ ባሕቲቶ ፡ ወይትለአክዎሙ ፡ ለቀሳውስት ፡ በመካን ፡ ኀበ ፡ ያጠምቅዎን ፡ ለአንስት ፡ እስመ ፡ ዘይደልዎን ፡ ዝ ፡ ውእቱ ።

፪፻፹ በዶስ ፡ ፮ቱ ፡ ወትኩን ፡ ዲያቆናዊት ፡ ክብርተ ፡ በኀቤክሙ ፡ ወኢትበል ፡ ምንተኒ ፡ እምቃል ፡ ወኢትግበር ፡ ምንተኒ ፡ ዘእንበለ በትእዛዘ ፡ ዲያቆን ፡ ወኢትሖር ፡ ብእሲት ፡ ኀበ ፡ ዲያቆን ፡ ወኢኀበ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ከመ ፡ ትስአል ፡ በእንተ ግብር ፡ ዘእንበለ ፡ ምስለ ፡ ዲያቆናዊት ።

፪፻፹፩ ዘ፴ወ፬ቱ ፡ ወዲያቆናዊት ፡ ትገሥፆን ፡ ለአን ስት ፡ ወታስርፎን ፡ ወትርድኦን ።

፪፻፹፪ ዶቅ ፡ ዘ፲ወ፩ዱ ፡ ወኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩና ፡ እምአንስት ፡ ውስተ ፡ መዓርገ ፡ ቅስና ፡ ወኢይ ስመያ ፡ በዝንቱ ፡ ስም ፡ ወኢይውጥና ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጸሎተ ፡ ወኢይፌጽማ ፡ ጸሎተ ፡ ለስርሖ ፡ ወኢይጸልያ ፡ በልዑል ፡ ቃል ።

፪፻፹፫ ራብዕ ፡ በእንተ ፡ ግብራት ፡ ዘትመትሮሙ ፡ ዘኢተጽሕፈ ፡ ውስተ ፡ አናቅጽ ፡ ቀዳማውያን ፡ ወውስተ ፡ አንቀጸ ፡ ካህናት ። በስ ፡ ዘ፵ወ፰ቱ ፡ አናጕንስጢስ ፡ ለእመ ፡ ሰረቀ ፡ ይስደድ ፡ በእ ንተ ፡ ስሕተተ ፡ ዘገብር ፡ ወይንበር ፡ ዓመተ ፡ ወኢያንብብ ፡ ሳልሰ ፡ አትሮንስ ፡ ወእምድኅ ረዝ ፡ ያንብብ ፡ ካዕበ ፡ ወኢይሠየም ፡ ውስተ ፡ መዓርግ ፡ ዳግማዊ ፡ አላ ፡ ይቁም ፡ በመዓር ጊሁ ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ሞቱ ፡ እስመ ፡ ተረክበ ፡ ውስቴቱ ፡ ስሕተት ፡ በመዓርግ ፡ ቀዳሚት ፡ ኢይደልዎ ፡ከመ ፡ ይትአመን ፡ ሳልሰ ፡ መዓ ርግ ፡ ዳግማዊ ። ዘ፸ወ፱ቱ ፡ ወለእመ ፡ ተምህረ ፡ ዘቢጠ ፡ መሰንቆ ፡ ያእምር ፡ ወይትአመን ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ኢይገብእ ፡ ኀበ ፡ ዝንቱ ፡ ወለ እመ ፡ ተመይጠ ፡ ምስሌሁ ፡ ዳግመ ፡ ይኩን ፡ ክቡነ እሁ ፡ ፯ተ ፡ ሱባዔ ። ወሶበ ፡ ፈቀደ ፡ ዘንተ ፡ ግብረ ፡ ከመ ፡ የሀሉ ፡ ቦቱ ፡ ይትመተር ፡ ወይሰ ደድ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያን ።

፪፻፹፬ ኃምስ ፡ በእንተ ፡ ዘይደሉ ፡ ሎሙ ፡ ረስጠብ ፡ ፲ወ፯ቱ ፡ አናጕንስጢሳውያን ፡ ወመዘምራን ፡

ስለ ፡ ንፍቀ ፡ ዲያቆን ።

፪፻፸፰ ጸኑ ፡ ፴፱ ። አርድእትና ፡ ጠባቂዎች ፡ ጽሙን፡ ማቀበል ፡ አይገባቸውም ።

፪፻፸፱ ረስጣ ፡ ፵፱ ። ዲያቆናውያት ፡ ሴቶች ፡ አይ ባርኩ ፡ ቀሳውስትና ፡ ዲያቆናትም ፡ ከሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ ወገን ፡ ምንም ፡ ምን ፡ አይሥሩ ። በሩን ፡ ብቻ ፡ ይጠብቁ ፡ እንጂ ። ሴቶችን ፡ በሚያጠምቁ በትም ፡ ቦታ ፡ ለቀሳውስት ፡ ይላኳቸው ፡ እንጂ ። የሚገባቸው ፡ ይህ ፡ ነውና ።

፪፻፹ በዶስ ፡ ፮ ። በናንተ ፡ ዘንድ ፡ ዲያቆናዊት ፡ የከበ ረች ፡ ትሁን ። ከቃል ፡ ወገን ፡ በቃል ፡ ምንም ፡ ምን ፡ አትበል ። ያለ ፡ ዲያቆኑ ፡ ትእዛዝ ፡ ምን ም ፡ ምን ፡ አትሥራ ። ሴት ፡ ከዲያቆናዊቱ ፡ ጋር ፡ ካልሆን ፡ በቀር ፡ ስለ ፡ ሥራ ፡ ትጠይቅ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ዲያቆንና ፡ ወደ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አትሂድ ።

፪፻፹፩ ፴፬ ። ዲያቆናዊት ፡ ሴቶችን ፡ ትምከራቸው ፡ ታሳርፋቸው ፡ ትርዳቸውም ።

፪፻፹፪ ዶቅ ፡ ፲፩ ። ከሴቶች ፡ ወገን ፡ የቅስና ፡ ማዕርግ ፡ ሊሾሩቸው ፡ አይገባም ። በዚህም ፡ ስም ፡ አይ ጠሩ ። በቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ጸሎትን ፡ አይጀ ምሩ ። ለማስናበት ፡ ጸሎቱን ፡ አይጨርሱ ። ጮኸውም ፡ አይጸልዩ ።

፪፻፹፫ አራተኛው ፡ ስለምትሽራቸው ፡ ነውር ፡ ይናገ ራል ። በቀደሙት ፡ አንቀጾችና ፡ በአንቀጸ ፡ ካህናት ፡ ያልተጻፈ ፡ ነው ። በስ ፡ ፵፰ ። አናጕን ስጢስ ፡ ቢሰርቅ ፡ ስላደረገው ፡ ስሕተት ፡ ይለይ ፡ ዓመትም ፡ ይቀመጥ ። በአትሮንስ ፡ ላይም ፡ አያንብብ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዳግመኛ ፡ ያንብብ ፡ ሁለተኛውን ፡ መዓርግ ፡ አይሾም ። እስከ ፡ ሚሞ ትበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ በዚያው ፡ በሹመቱ ፡ ይኑር ፡ እንጂ ። በመጀመሪያዪቱ ፡ መዓርግ ፡ ስሕተት ፡ ተገኝቶበታልና ፡ በሁለተኛ ፡ ማዕ ርግ ፡ ላይ ፡ ይታመን ፡ ዘንድ ፡ አይገባውም ። ፸፱ ፡ መሰንቆ ፡ መምታት ፡ ቢማር ፡ እርሱ ፡ ወደዚህ ፡ እንደማይገባ ፡ ይወቅ ፡ ይታመንም ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ቢመለስ ፡ ቅጣቱ ፡ ፯ ፡ ሱባዔ ፡ ይሁን ። ይናርበት ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ ቢወድ ፡ ይሻር ። ከቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ይለይ ።

፪፻፹፬ አምስተኛው ፡ ስለሚገባቸው ፡ ይናገራል ። ረስ ጠብ ፡ ፲፯ ፡ አናጕንስጢሳውያንና ፡ መዘም

ስእመ ፡ ቦኡ ፡ ወፈቀዱ ፡ ከመ ፡ ያውስቡ ፡ ብእሲተ ፡ ሰያውስቡ ። በስ ፡ ዘ፺ወ፭ቱ ፡ ወሶበ ፡ ሞተት ፡ ብእሲቶሙ ፡ ለእናጕንስጢሳውያን ፡ ወመዘምራን ፡ ወዐቀብተ ፡ አናቅጽ ፡ እሙንቱ ፡ ብዉሐን ፡ ከመ ፡ ያውስቡ ።



ራን ፡ ተመልሰው ፡ ሚስት ፡ ሊያገቡ ፡ ቢወዱ ፡ ያግቡ ። በስ ፡ ፺፭ ። እናጕንስጢሳውያን ፡ መዘምራንና ፡ በረኞች ፡ ሚስታቸው ፡ በሞተችባቸው ፡ ጊዜ ፡ እነሱ ፡ ሊያገቡ ፡ ይገባቸዋል ።

## አንቀጽ ፡ ታስዕ ።

በእንተ ፡ ኵሎሙ ፡ ካህናት ፡ ወተላውያኒሆሙ ፡ ዘውዑእ ፡ እምነ ፡ ዘተፈልጠ ፡ እምአናቅጺሆሙ ፡ ለቀደምት ።

፪፻፸፭ ወውእቱ ፡ ፰ቱ ፡ አክፋል ፡ ቀዳማዊ ፡ በእንተ ፡ ዘይደሉ ፡ ሎቱ ፡ ክህነት ፡ ወዘይከልእ ፡ እምኔሁ ። ረስጠብ ፡ ዘ፸ወ፩ዱ ፡ ወበትነቢሶ ፡ አኮ ፡ ኵሉ ፡ ዘይፈቅድ ፡ ይምላእ ፡ ውስተ ፡ እደዊነ ፡ ከመ ፡ ይንሣእ ፡ እምኔነ ፡ ዘይፈቅዶ ።

፪፻፸፮ ዘኒቅያ ፡ ዘ፩ዱ ፡ ለዘገዘርዎ ፡ እምድኅረ ፡ ጥምቀት ፡ አው ፡ ሐጸውዎ ፡ በግብር ፡ አው ፡ በምክንያተ ፡ ደዌ ፡ ገብረ ፡ ሎቱ ፡ ዘንተ ፡ ዐቃቤ ፡ ሥራይ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትትዌከፎሙ ። ወለእመ ፡ ይደልዎሙ ፡ ነሢአ ፡ ክህነት ፡ ወዘሰ፡ ገብረ ፡ ዘንተ ፡ በፈቃደ ፡ ርእሱ ፡ ዘእንበለ ፡ ምክንያተ ፡ ደዌ ፡ ኢይኩን ፡ ካህነ ።

፪፻፸፯ ረስጠጅ ፡ ዘ፸ወ፯ቱ ፡ ኢይሠየሙ ፡ አግብርት ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ በምንትኒ ፡ እምግብረ ፡ መልእክተ ፡ ክህነት ፡ ዘእንበለ ፡ በፈቃደ ፡ አጋእዝቲሆሙ ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ በእንተ ፡ ኀዘነ ፡ አጋእዝቲሆሙ ፡ ወንሥተተ ፡ ቤቶሙ ። እመሰ ፡ ኮነ ፡ ውእቱ ፡ ገብር ፡ ዘይሤኒ ፡ ለክህነት ፡ ከመ ፡ አናሲሞስ ፡ ወአግዐዞ ፡ እግዚኡ ፡ ወአብሐ ፡ ከመ ፡ ይፃእ ፡ እምቤቱ ፡ ወበቅድመ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ አግዐዞ ፡ ግዕዛነ ፡ ክሡተ ፡ ወኮነ ፡ ድልወ ፡ ይሠየም ።

፪፻፸፰ ዘ፳ወ፬ቱ ፡ ወምእመን ፡ ክርስቲናዊ ፡ እመ ፡ ተሞቅሐ ፡ በእንተ ፡ ስመ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢያንብሩ ፡ ላዕሌሁ ፡ እደ ፡ ሰመልእክተ ፡ ዲቁና ፡ ወቅስና ፡ እስመ ፡ ሎቱ ፡ ክብረ ፡ ቅስና ፡ በተአምኖ ፡ ዘስምዕ ። ወለእመሰ ፡ ተሠይመ ፡ ኢጲስቆጶስና ፡ ያንብሩ ፡ እደ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወለእመሰ ፡ ኮነ ፡ ተአማኔ ፡ ወኢቦአ ፡ ኀበ ፡ ንገሥታት ፡ ወኢተኰነነ ፡ በማእሰራት ፡ ወበሙቃሔ ፡ ወኢ

## አንቀጽ ፡ ፱ ።

ስለ ፡ ካህናትና ፡ ስለ ፡ ተከታዮቻቸው ፡ ሁሉ ። ከቀደሙት ፡ አናቅጽ ፡ ተለይቶ ፡ የተውጣጣ ።

፪፻፸፭ ይኸውም ፡ ፰ ፡ ክፍል ፡ ነው ። መጀመሪያው ፡ ክህነት ፡ ስለሚገባውና ፡ ከመቀበልም ፡ ስለሚከለክለው ፡ ይናገራል ። ረስጠብ ፡ ፸፩ ። በእኛ ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ እጅ ፡ ሙሉ ፡ ሊሰጠን ፡ የሚወድ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚሻውን ፡ ከእኛ ፡ የሚቀበል ፡ አይደለም ።

፪፻፸፮ ኒቅያ ፡ ፩ ። ከጥምቀት ፡ በኋላ ፡ የገዘፉትን ፡ ወይም ፡ በግድ ፡ የሰለቡትን ፡ ወይም ፡ በደዌ ፡ ምክንያት ፡ ሐኪም ፡ ይህን ፡ ያደረገለትን ፡ ክህነትን ፡ ለመቀበል ፡ የበቁ ፡ ከሆኑ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትቀበላቸዋለች ። ያለ ፡ ደዌ ፡ ምክንያት ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ ይህን ፡ ያደረገ ፡ ግን ፡ ካህን ፡ አይሁን ።

፪፻፸፯ ረስጠጅ ፡ ፸፯ ። ባሪያዎች ፡ ያለ ፡ ጌቶቻቸው ፡ ፈቃድ ፡ ከክህነት ፡ አገልግሎት ፡ ሥራ ፡ ወገን ፡ በማናቸውም ፡ ሁሉ ፡ አይሾሙ ። ይህ ፡ ጌቶቻቸው ፡ ስለሚያዝኑ ፡ ነውና ፡ ቤታቸውም ፡ ስለሚፈርስ ፡ ነውና ። ባሪያው ፡ ለክህነት ፡ እንደ ፡ አናሲሞስ ፡ የበቃ ፡ ጌታውም ፡ ነፃ ፡ ያወጣው ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ከቤቱም ፡ ይወጣ ፡ ዘንድ ፡ ቢያሰናብተው ፡ በሰውም ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ በግልጽ ፡ ነፃ ፡ ካወጣው ፡ ዝግጁም ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘ ፡ ይሾም ።

፪፻፸፰ ሾ፬ ። ክርስቲያናዊ ፡ አማኝ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ቢታሠር ፡ በቅስናና ፡ በዲቁና ፡ ለማገልገል ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ እጅ ፡ አያኑሩ ። በሃይማኖት ፡ ምስክርነት ፡ የቅስና ፡ መዓርግ ፡ አለውና ። ኢጲስቆጶስነትን ፡ ቢሾም ፡ ግን ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ እጅ ፡ ያኑሩ ። አማኒ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ነገሥታትም ፡ ባይገባ ፡ በእሥራትም ፡ ባይፈረድበት ፡ መከራም ፡ ባያገኘው ፡ ነገር ፡

ረከቦ ፡ ምንዳቤ ፡ እላ ፡ ምስለ ፡ ኵሉ ፡ ሶበ ፡ ተሰደ ፡ ወተመነነ ፡ በእንተ ፡ እግዚእ ፡ ወተኰነነ ፡ ኵነኔ ። በውስተ ፡ ቤቱ ፡ እንዘ ፡ ይትአመን ፡ ውእቱ ፡ ድልው ፡ ለኵሉ ፡ መዓርገ ፡ ክህነት ፡ ወያንብሩ ፡ እደ ፡ ላዕሌሁ ።

፲፻፷፱ በስ ፡ ፵ወ፱ቱ ፡ ዘ፶ ፤ ወኢይትከላእ ፡ ብእሲ ፡ እምነ ፡ ሢመት ፡ በእንተ ፡ ነውረ ፡ ሥጋሁ ፡ እመ ፡ ኮነ ፡ ነቋረ ፡ አው ፡ ሐንካሰ ፡ አው ፡ ኮነ ፡ ፀጋመ ፡ እድ ፡ እመ ፡ ይከሉ ፡ ይቀድሱ ፡ ወኮኑ ፡ ድልዋነ ፡ ወዘሂ ፡ ተሀበለ ፡ ወከልእሙ ፡ ውእቱ ፡ ይፃእ ፡ እስከ ፡ ይትዌከፎሙ ።

፲፻፸ ዘ፶ወ፭ቱ ፡ ወለሕዝባዊኒ ፡ ሶበ ፡ ኮኑ ፡ ሎቱ ፡ ስምዐ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ድልው ፡ ለንሢእ ፡ መዓርገ ፡ ቅስና ፡ ኢይስድድዎ ፡ በእንተ ፡ ዘኢኮነ ፡ እምዘመደ ፡ ካህናት ፡ እስመ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወለደቶሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ በጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ ወረድፋደሰ ፡ ለዓቃብያነ ፡ ሕግ ፡ እስመ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ስምዐ ፡ ኮነ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ከመ ፡ እለ ፡ ተጠምቁ ፡ በክርስቶስ ፡ ፩ዱ ፡ እሙንቱ ።

፲፻፸፩ ረስጠጅ ፡ ፲ወ፰ቱ ፡ ዘ፲ወ፯ቱ ፡ ረስጠብ ፡ ዘ፲ወ፫ቱ ፡ ወዘአውሰበ ፡ ዳግመ ፡ እምድኅረ ፡ ጥምቀት ፡ አው ፡ ገብረ ፡ ዕቅብተ ፡ እምድኅረ ፡ አውሰበ ፡ ብእሲተ ፡ በከሡት ፡ አው ፡ በኅቡእ ፡ አው ፡ አውሰበ ፡ መዓስብተ ፡ አው ፡ ፪ተ ፡ አኃተ ፡ አው ፡ ዘይትሔዘብዋ ፡ በርኵስ ፡ አው ፡ ዘማዊተ ፡ አው ፡ አመተ ፡ አው ፡ ዘተሐውር ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ተውኔት ፡ አው ፡ ኅድግተ ፡ አው ፡ ዘይሔምይዋ ፡ ኢይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አው ፡ ቀሲስ ፡ አው ፡ ዲያቆነ ፡ አው ፡ ፩ደ ፡ እምሥዩማን ።

፲፻፸፪ ረስጠጅ ፡ ዘ፳ወ፳ቱ ፡ ዘ፸ወ፩ዱ ፡ ረስጠጅ ፡ ዘ፵ወ፪ቱ ፡ ዘ፶ወ፩ዱ ፡ እመቦ ፡ ብእሲ ፡ እምእመናን ፡ ዘአስተዋደይዎ ፡ በእንቲአሁ ፡ በምንትኒ ፡ ምክንያት ፡ እምክንያተ ፡ ዝሙት ፡ ወምርዓት ፡ ወዓመፃ ፡ ወዘይመስሎ ፡ ለዝንቱ ፡ እምግብረ ፡ ኀፍረት ፡ ወዘተዛለፍዎ ፡ በገሃድ ፡ ኢይሠየም ፡ ምንተኒ ፡ እመዓርገ ፡ ክህነት ። ወዘሂ ፡ ያወድቆ ፡ ጋኔን ፡ ኢይኩን ፡ ሥዩመ ፡ በመዓርገ ፡ ክህነት ፡ ወኢይጸሊ ፡ ምስለ ፡ ምእመናን ። ወእምድኅረ ፡ ተፈወሰ ፡ ወኢተመይጠ ፡ ኀቤሁ ፡ ዳግመ ፡ ይደልዎ ፡ ሢመተ ፡ ክህነት ።

፲፻፸፫ ዘኒቅያ ፡ ፫ቱ ፤ ወዘኮነ ፡ ሐዲስ ፡ ሃይማኖት ፡



ግን ፡ ስለጌታው ፡ ከሁሉ ፡ ጋር ፡ ቢሰደድና ፡ ቢናቅ ፡ አምኖም ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ቅጣትን ፡ ቢቀጣ ፡ እርሱ ፡ ለመዓርገ ፡ ክህነት ፡ የተገባ ፡ ነው ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ እጅ ፡ ያኑሩ ።

፲፻፷፱ በስ ፡ ፵፱ ፡ ፶ ። ሰው ፡ ስለ ፡ ሥጋው ፡ ነውር ፡ ከሹመት ፡ አይከልከል ። አንድ ፡ ዓይና ፡ ወይም አንካሳ ፡ ወይም ፡ ግራኝ ፡ ቢሆን ፡ ይቀድሱ ፡ ዘንድ ፡ የሚችሉና ፡ የተገባቸው ፡ ከሆኑ ፡ አይከልከሉ ። ተደፋፍሮ ፡ የከለከላቸውም ፡ ቢኖር ፡ እስኪቀበላቸው ፡ ድረስ ፡ ይለይ ።

፲፻፸ ፶፭ ። ሕዝባዊም ፡ የቅስናን ፡ መዓርግ ፡ ለመቀበል ፡ እርሱ ፡ ዝግጁ ፡ እንደሆነ ፡ ቢመሰክሩለት ፡ ከካህናት ፡ ወገን ፡ ስላይደለ ፡ አይለዩት ። ሁላቸውን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በክርስትና ፡ ጥምቀት ፡ ወልዳቸዋለችና ። ይልቁንም ፡ ሕግን ፡ ለሚጠብቁ ፡ ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ የተጠመቁ ፡ በክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ ሲል ፡ መስክሮአልና ። (ሮሜ ፡ ፮ ፡ ፫) ።

፲፻፸፩ ረስጠጅ ፡ ፲፰ ፡ ፲፯ ። ረስጠብ ፡ ፲፫ ። ከጥምቀት ፡ በኋላ ፡ ሁለተኛ ፡ ያገባ ፡ ሚስት ፡ካገባ ፡ በኋላ ፡ በግልጥ ፡ ወይም ፡ በሽሽግ ፡ ዕቁባት ፡ ያበጀ ፡ ወይም ፡ ፈቷን ፡ ወይም ፡ እትማማቾችን ፡ ያገባ ፡ ወይም ፡ በዝሙት ፡ የሚጠረጥሩዋትን ፡ ወይም ፡ ዘማዊቱን ፡ ወይም ፡ ባሪያይቱን ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ጨዋታ ፡ ቤት ፡ የምትሄደውን ፡ ወይም ፡ የተፈታችውን ፡ ወይም ፡ የሚያሙዋትን ፡ ያገባ ፡ ሰው ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወይም ፡ ቄስ ፡ ወይም ፡ ዲያቆን ፡ ወይም ፡ ከሹማምንት ፡ አንዱ መሆን ፡ አይገባውም ።

፲፻፸፪ ረስጠጅ ፡ ፳፳ ፡ ፸፩ ። ረስጠጅ ፡ ፵፪ ፡ ፶፩ ። ከዝሙት ፡ ምክንያት ፡ ወገን ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ በርሱ ፡ ከምእመናን ፡ ወገን ፡ የከሰሱት ፡ ቢኖር ፡ በመዳራት ፡ በዐመፅ ፡ ከሚያሳፍር ፡ ሥራ ፡ ወገን ፡ ይህን ፡ በሚመስል ፡ በግልጽ ፡ የረቱት ፡ ሰው ፡ ከክህነት ፡ መዓርግ ፡ ወገን ፡ ምንም ፡ ምን ፡ አይሾም ። ጋኔን ፡ የሚጥለው ፡ በክህነት ፡ መዓርግ ፡ ሹም ፡ አይሁን ። ከምእመናንም ፡ ጋር ፡ አይጸልይ ። ከዳነ ፡ በኋላ ፡ ግን ሁለተኛ ፡ ካልተመለሰበት ፡ የክህነት ፡ ሹመት ፡ ይገባዋል ።

፲፻፸፫ ኒቅያ ፡ ፫ ። አዲስ ፡ አማኝ ፡ የሆነ ፡ እስኪማርና ፡

ኢያኩን ፡ ካህን ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ይትጌሠጽ ፡ ወይትሐተት ፡ ገድሉ ፡ ወጥያቄ ፡ ሃይማኖቱ ፡ ወጽርየተ ፡ ተኃርዮቱ ፡፡ እስመ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ይቤ ፡ "ወኢይኩን ፡ ተክለ ፡ ሐዲስ ፡ ከመ ፡ ኢይትዐበይ ፡ ወኢይደቅ ፡ ውስተ ፡ ፍትሐ ፡ ዲያብሎስ" ፡ ወእመ ፡ ኮነ ፡ ዘኀለፈ ፡ መዋዕለ ፡ ነዊኀ ፡ ወእምድኅረዝ ፡ ተከሥተት ፡ ላዕሌሁ ፡ ኃጢአት ፡ ነፍሳዊት ፡ ዘከመ ፡ ድካመ፡ ሃይማኖት ፡ አው ፡ ተሊወ ፡ ቃል ፡ መስተቃርን፡ አው ፡ ተኀየየ ፡ እምዘይደሉ ፡ ላዕሌሁ ፡ ኢይኩን ፡ በምንትኒ ፡ እመዓርገ ፡ ክህነት ፡፡

፪፻፹፬ ዘዮሐንስ ፡ ፳ቱ ፡ በእንተ ፡ ፍርሃት ፡ ሠናይት ፡ ወፈሪሀ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሠናይ ፡ ውእቱ ፡ ወኢይደልዎ ፡ ለብእሲ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ሊቀ ፡ ለእመ፡ ኢኮነ ፡ ፈራሄ ፡ ወለባዌ ፡ እስመ ፡ አነ ፡ አአምር፡ ከመ ፡ ብዙኃን ፡ ሰብእ ፡ ሞቅሑ ፡ ነፍሳቲሆሙ ፡ በኵሉ ፡ አዝማን ፡ እስከ ፡ አውደቁ ፡ ነፍሳቲሆሙ ፡ በጾም ፡ ወነበሩ ፡ በኵሉ ፡ ምግባሮሙ ፡ ባቲ ፡ እንዘ ፡ ኢያስተሐምሙ ፡ ለካልኣኒሆሙ ፡ ይትወሰኩ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወያፈደፍዱ ፡ በገቢረ ፡ ፍትሕ ፡ ንኡሰ ፡ ወሶበ ፡ ቀርቡ ፡ ኀበ ፡ ክህነት ፡ ወአገበርዎሙ ፡ አርትዖ ፡ ጥውየቶሙ ፡ ለካልኣን ፡ ኢክህሉ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ በእንተ ፡ ውእቱ ፡ ግሙራ ፡ ወጐዩ ፡ ወቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘአገበርዎ ፡ ከመ ፡ ይሠየም ፡ ወገደፈ ፡ እምኔሁ ፡ ጽድቀ ፡ ዘቀዳሚ ፡ ውነኮለ ፡ ኀጉለ ፡ ዐቢየ ፡፡ ወኢቦአ ፡ ኀበ ፡ ክህነት ፡ እምድኅረ ፡ ልህቀ ፡ በመዓርግ ፡ ማእከላዊ ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ይከውን ፡ ድልወ ፡ ለዝንቱ ፡፡

፪፻፹፭ ወዳግማዊ ፡ በእንተ ፡ ሢመቱ ፡ ድስቅ ፡ ፲ወ፺ቱ፡ ንኤዝዘክሙ ፡ ከመ ፡ ይሠየም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እም፫ቱ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዐበዘ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ይሠየም ፡ እም፪ቱ ፡ እም፩ዱስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይሠየም ፡ እስመ፡ በስምዐ ፡ ፪ቱ ፡ አው ፡ ፫ቱ ፡ ይጸንዕ ፡ ወይትከሠት ፡ ኵሉ ፡ ግብር ፡ ፈድፋደ ፡፡ ለቀሳውስትሰ ፡ ወለዲያቆናት ፡ ይሢሞሙ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ባሕቲቱ ፡ ወከማሁ ፡ ካዕበ ፡ ለእለ ፡ ተርፉ ፡ ሥዩማን ፡ ቀሳውስትስ ፡ ወዲያቆናት ፡ ኢይሢሙ ፡ ፩ደሂ ፡ እምሕዝባውያን ፡ ካህን ፡፡ ዘ፳ወ፩ዱ ፡ ወኢ፩ደሂ ፡ እምሥዩማን ፡፡ በስ ፡ ፹ወ፮ቱ ፡ ወኢይሠየም ፡ ፩ሂ ፡ ዘእንበለ ፡ ይኩንዎ ፡ ስምዐ ፡፡



ትሩፋቱ ፡ እስኪመረመር ፡ የሃይማኖቱ ፡ መረዳትና ፡ የመመረጡ ፡ ንጽሕና ፡ እስኪታወቅ ፡ ድረስ ፡ ካህን ፡ አይሁን ፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ፡ "እንዳይታበይ ፡ በዲያብሎስም ፡ ፍርድ ፡ እንዳይወድቅ ፡ አዲስ ፡ አማኝ ፡ አይሁን" ፡ ብሏልና ፡፡ (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፮-፯) ፡ ብዙውን ፡ ዘመን ፡ ያሳለፈ ፡ ቢሆን ፡ ሃይማኖቱ ፡ ደካማ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ የነፍስ ፡ ኃጢአት ፡ ወይም ፡ የጠብ ፡ የክርክር ፡ ቃል ፡ ቢገለጥበት ፡ ወይም ፡ ለርሱ ፡ የሚገባውን ፡ ችላ ፡ ቢል ፡ ከክህነት ፡ መዓርግ ፡ ወገን ፡ በማናቸውም ፡ አይሾም ፡፡

፪፻፹፬ ዮሐንስ ፡ ፳ ፡፡ ስለ ፡ በጎ ፡ ፍርሃት ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ መልካም ፡ ነው ፡፡ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፈሪና ፡ አስተዋይ ፡ ካልሆነ ፡ አለቃ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ አይገባውም ፡፡ ሰውነታቸውን ፡ በጾም ፡ እስከመጐዳት ፡ ደርሰው ፡ በዘመን ፡ ሁሉ ፡ ሰውነታቸውን ፡ ወስነው ፡ ገትተው ፡ ብዙ፡ ሰዎች ፡ እንደያዙ ፡ እኔ ፡ አውቃለሁና ፡፡ የተባሕትዎንም ፡ ሥራ ፡ ያበዛሉ ፡፡ ወደ ፡ ክህነት ፡ በቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ የሌሎችንም ፡ ጥመት ፡ ያቃኑ ፡ ዘንድ ፡ ግድ ፡ ባሏቸው ፡ ጊዜ ፡ ከነርሱ ፡ አንዱ ፡ ስለነርሱ ፡ ፈጽሞ ፡ አልቻለም ፡፡ ሸሹም ፡፡ ከነርሱም ፡ ይሾም ፡ ዘንድ ፡ ግድ ፡ ያሉት ፡ አለ ፡፡ የቀደመ ፡ ክብሩን ፡ ተወ ፡፡ ፍጹም ፡ ጥፋትንም ፡ ጠፋ ፡፡ ለዚህ ፡ አስኪበቃ ፡ ድረስ ፡ በማእከላዊ ፡ መዓርግ ፡ ከኖረ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ክህነት ፡ አልተመለሰም ፡፡

፪፻፹፭ ሁለተኛው ፡ ስለ ፡ ሹመት ፡ ይናገራል ፡፡ ድስቅ ፡ ፲፺ ፡፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ከ፫ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ እንዲሾም ፡ እናዝዛችኋለን ፡፡ የኤጲስቆጶሳት ፡ ችግር ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ከሁለት ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ይሾም ፡፡ ከአንድ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ግን ፡ ይሾም ፡ ዘንድ ፡ አይገባም ፡፡ በሁለት ፡ ወይም ፡ በሦስት ፡ ምስክር ፡ ነገር ፡ ይጸናልና ፡፡ ፈጽሞ ፡ ሥራው ፡ ሁሉ፡ ይገለጣልና ፡፡ ቀሳውስትንና ፡ ዲያቆናትን ፡ ግን፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ ብቻ ፡ ይሹማቸው ፡፡ ዳግመኛም ፡ የቀሩትን ፡ ሹማምንት ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ፡፡ ቀሳውስትና ፡ ዲያቆናት ፡ ግን ፡ ከሕዝቡ ፡ ወገን ፡ አንዱንስ ፡ እንኳ ፡ አይሹሙ ፡፡ ፳፩ ፡ ከሹማምቱም ፡ ወገን ፡ አንዱንስ ፡ እንኳ ፡ በስ ፡ ፹፮ ፡፡ አንዱስ ፡ እንኳ ፡ ሳይመሰክሩለት ፡ አይሾም ፡፡

አንቀጽ ፡ ፱ ።

፪፻፹፮ ዘኒቅያ ፡ ፳ወ፬ቱ ፡ ወእለሰ ፡ ተኅርዩ ፡ እምኅ ባኤ ፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ ካህናተ ፡ ወያትባርኩ ፡ እምኤጲስቆጶስ ፡ ያምጽእሙ ፡ ሊቀ ፡ ዲያቆናት ፡ ኀበ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወያመክሮሙ ፡ ቅድመ ለኵሎሙ ፡ ወይርአዮሙ ፡ እመ ፡ ኮኑ ፡ ማእምራነ ፡ በአንብቦ ፡ መጻሕፍት ፡ ወተምህሩ ፡ ሕገገ ፡ ክህነት ፡ ወይምጽኡ ፡ እምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ወያመክሮሙ ፡ ወየአዝዞሙ ፡ ፍጹመ ። ወሊቀ ፡ ዲያቆናትሰ ፡ ውእቱ ፡ ማእምር ፡ ወመገሥጽ ፡ ለብእ ፡ ሀገር ፡ ወኵሎሙ ፡ ወዲያቆናት፡ ወለሊሁ ፡ ሊቀ ፡ ጸሎት ፡ ወኵሉ ፡ ዲቁና ፡ ወኮሬ ፡ አቢስኮቦስኒ ፡ ውእቱ ፡ ሊቀ ፡ እንባቢ ፡ በጊዜ ፡ ጸሎት ።

፪፻፹፯ ዘ፳ወ፮ ፡ ወኢይኩኑ ፡ ውኁዳነ ፡ ካህናት ፡ ውስተ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከመ ፡ ኢይሕጽጹ ፡ ለጸሎት፡ ወለመልእክት ፡ ወዓዲ ፡ ኢይኅሥር ፡ መንበር ፡ ወኢይብዝኁ ፡ ካዕበ ፡ ከመ ፡ ኢይሕጽጽ ፡ ሲሳይ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አላ ፡ ይኅረዩ ፡ መጋቢያኒሃ ፡ በአምጣነ ፡ የአክላ ፡ በዝንቱ ።

፪፻፹፰ ማልስ ፡ በእንተ ፡ መዓርጊሆሙ ። ይቤሉ ፡ ሐዋርያት ፡ በጥንተ ፡ ዲድስቅልያ ። ንሕነ ፡ ሐዋርያት ፡ ተጋቢአነ ፡ ውስተ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ አንበርነ ፡ ዘንተ ፡ ትምህርተ ፡ ወሰመይነ ፡ ኵሎ ፡ መዓርጋተ ፡ በበድልወታት ፡ በአምሳለ ፡ ሰማያውያን ። ወከማሁ ፡ ትኩን ፡ ካዕበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወለይንበር ፡ ኵሉ ፡ ለለ፩ዱ ፡ ውስተ ፡ ዘተሠይመ ፡ ሎቱ ፡ እምእግዚአብሔር ። ወይኩን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ከመ ፡ ኖላዊ ። ወቀሳውስት ፡ በአምሳለ ፡ መምህራን ፡ ዲያቆናትኒ ፡ ከመ ፡ ላእካን ፡ ወንፉቀ ፡ ዲያቆናት ፡ ከመ ፡ ረዳእያን ፡ ወእናግኖንስጢሳውያን ፡ እንባብያን ፡ ወአብስሊዲያሳውያን ፡ መዘምራን ፡ እሊፍሉሳውያን ፡ ዐጸውተ ፡ አንቀጽ ፡ ወእሙንቱ ፡ እምሕዝብ ።

፪፻፹፱ ዘ፱ቱ ፡ እስመ ፡ ነገሥት ፡ ዘነበሩ ፡ በዘመነ ፡ ብሊት ፡ ኮኑ ፡ ይሜግቡ ፡ ሠራዊተ ፡ ወየኀድጉ ፡ ጸብአ ፡ ወየኀሥሡ ፡ ዕርቀ ፡ ለዕቅበተ ፡ ሥጋ ። ወኤጲስቆጶስሰ ፡ ዘነሥአ ፡ ክህነተ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ይዕቀብ ፡ ሥጋ ፡ ወነፍሰ ፡ እምኀጕል ፡ በከመ ፡ ነፍስ ፡ ትከብር ፡ እምሥጋ ፡ ከማሁ ፡ ክህነትኒ ፡ ትትሌዓል ፡ በክብር ፡ እመንግሥት ። ወይእቲ ፡ ተእሥሮ ፡ ለዘይደልዎ ፡ ኵነኔ ፡ ወትፈትሖ ፡ ለዘይደልዎ ፡ ፍትሐት ።

ስለ ፡ ካህናት ፡ ሁሉ ።

፪፻፹፮ ኒቅያ ፡ ፳፬ ። ካህናት ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ በጉባኤ ፡ የተመረጡ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ከኤጲስቆጶሱ ፡ ይሾሙ ፡ ዘንድ ፡ ሊቀ ፡ ዲያቆኑ ፡ ወደ ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ ያምጣቸው ። አስቀድሞ ፡ ሁሉንም ፡ ይፈትናቸው ። መጻሕፍትን ፡ በማንበብ ፡ አዋቂዎች ፡ የክህነትንም ፡ ሕግ ፡ የተማሩ ፡ እንደ ሆኑ ፡ ይመርምራቸው ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ይምጡ ። ፈጽሞ ፡ ይዘዛቸው ፡ ይፈትናቸውም ። ሊቀ ፡ ዲያቆናት ፡ ግን ፡ አዋቂ ፡ የአገሩን ፡ ሰውና ፡ ዲያቆናትን ፡ ሁሉ ፡ አስተማሪ ፡ ነው ። እርሱ ፡ የጸሎትና ፡ የዲቁና ፡ ሁሉ ፡ አለቃ ፡ ነው ፡ እሱን ፡ ቀሲሱም ፡ (ኮሬ ፡ አቢስኮቢስ) ፡ በጸሎት ፡ ጊዜ ፡ የአንባቢ ፡ አለቃ ፡ ነው ።

፪፻፹፯ ፳፮ ። ለጸሎትና ፡ ለአገልግሎት ፡ እንዳይጎድሉ ፡ ካህናት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ያነሱ ፡ አይሁኑ ። ዳግመኛም ፡ በታው ፡ አይዋረድ። ዳግመኛም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ምግብ ፡ እን ዳያንስ ፡ አይብዙ ። በዚህ ፡ በሚቻላት ፡ መጠን ፡ ሹማምቶቿን ፡ ይምረጡ ፡ እንጂ ።

፪፻፹፰ ሦስተኛው ፡ ስለ ፡ መዓርጋቸው ፡ ይናገራል ። ሐዋርያት ፡ በዲድስቅልያ ፡ መጀመሪያ ፡ እን ዲህ ፡ አሉ ። እኛ ፡ ሐዋርያት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተሰብስበን ፡ ይህን ፡ ትምህርት ፡ አስቀመጥን ፡ በሰማያውያን ፡ አምሳል ፡ መዓርጋትን ፡ ሁሉ ፡ በየአንባቡ ፡ ሰየምን ። ዳግመኛም ፡ ቤተ ፡ ክርስ ቲያን ፡ እንደዚህ ፡ ትሁን ፡ ሁሉም ፡ እያንዳንዱ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በተሾመው ፡ ይኑር ። ኤጲስ ቆጶስ ፡ እንደ ፡ ጠባቂ ፡ ቀሳውስትም ፡ በመምህ ራን ፡ አምሳል ፡ ዲያቆናትም ፡ እንደ ፡ አገልጋ ዮች ፡ ንፉቀ ፡ ዲያቆናት ፡ እንደ ፡ ረዳቶች ፡ አናግኖንስጢሳውያን ፡ አንባቢዎች ፡ አቡሊዲሳ ውያን ፡ መዘምራን ፡ አሊፍሉሳውያን ፡ በር ፡ ዘጊዎች ፡ ይሁኑ ። እነርሱም ፡ ከሕዝቡ ፡ ወገን ናቸው ።

፪፻፹፱ ፱ ፡ በዘመነ ፡ ብሉይ ፡ የነበሩ ፡ ነገሥታት ፡ ሠራ ዊቱን ፡ ያስተዳድሩ ፡ ነበር ፡ እኮ ፡ ጠብ ፡ ከርክ ርን ፡ ትተው ፡ ሥጋን ፡ ለመጠበቅ ፡ እርቅን ይሻሉ ። ኤጲስቆጶስ ፡ ግን ፡ ከእግዚአብሔር የተሾመው ፡ ሥጋንና ፡ ነፍስን ፡ ከጥፋት ፡ ይጠ ብቅ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ነፍስ ፡ ከሥጋ ፡ እንደም በልጥ ፡ እንደዚሁም ፡ ክህነት ፡ በክብር ፡ ከመ ንግሥት ፡ ትበልጣለች ። ይህችውም ፡ ቅጣት ፡ የሚገባውን ፡ ትቀጣዋለች ፡ መፈታት ፡ የሚ

፪፻፺ ፴ወ፪ቱ ፡ ወሶበ ፡ ኮነ ፡ ዘይትቀወሞ ፡ ለንጉሥ ፡ ይደልዎ ፡ ከነኔ ፡ እመኒ ፡ ኮነ ፡ ወልዱ ፡ አው ፡ ፍቁሩ ፡ እፎ ፡ ፈድፋደ ፡ ዘይትቀወሞሙ ፡ ለካህናት ። ወበከመ ፡ ክህነት ፡ ትትሌዓል ፡ እመንግሥት ፡ ወከማሁኬ ፡ ኰነኔሁ ፡ ለዘይትቃረና ፡ ለክህነት ፡ ይፈደፍድ ፡ እምኰነኔሁ ፡ ለዘተቃወሞ ፡ ለንጉሥ ። ወእልቦ ፡ ፩ዱኒ ፡ ዘይድኅን ፡ እምኰነኔ ፡ ፪ሆሙ ፡ በከመ ፡ ኢድኅኑ ፡ አቤሴሎም ፡ ወአሚናዳብ ፡ እምኰነኔ ። ወኢቆሬ ፡ ወዳታን ፡ ወአቤሮን ። እስመ ፡ እልክቱ ፡ ተቃወምዎ ፡ ለዳዊት ፡ ንጉሥ ፡ ወእልክቱኒ ፡ ተቃወምዎሙ ፡ ለሙሴ ፡ ወአሮን ።

፪፻፺፩ ረሰጠጅ ፡ ፴ወ፱ቱ ፡ ወይቁም ፡ ኵሉ ፡ ለለ፩ዱ ፡ በውስተ ፡ መዓርግ ፡ ዘተውህበ ፡ ሎቱ ፡ ወኢይትዐገል ፡ ፩ዱሂ ፡ እምኔክሙ ፡ መዓርገ ፡ ካልኡ ፡ ዘኢተውህቦ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ታምዕዕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በአምሳለ ፡ ቆሬ ፡ ወዖዝያን ፡ ንጉሥ ። እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ተዐገሉ ፡ መዓርገ ፡ ክህነት ፡ ዘእንበለ ፡ ትእዛዘ ፡ እግዚአብሔር ። ወእልክቱኒ ፡ ውዕዩ ፡ በእሳት ፡ ወለንጉሥኒ ፡ ተሠርገወ ፡ ገጹ ፡ በለምጽ ። ወሙሴኒ ፡ ዘተናግሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወሰነ ፡ ዘይደሉ ፡ ከመ ፡ ይትፈጸም ፡ ሢመተ ፡ ክህነት ፡ ወዘይከውን ፡ እመንገሌሁ ፡ ካህን ፡ ወፈለጠ ፡ ኵሎ ፡ ለለ፩ዱ ፡ በከመ ፡ ይደሉ ። ወዘይደሉ ፡ ለሌዋውያን ፡ ቦቱ። ወሶበ ፡ ተዐደወ ፡ ፩ዱሂ ፡ ውዑእ ፡ እመልእክቱ፡ እንተ ፡ ተወክፋ ፡ ኰነኔሁ ፡ ሞት ።

፪፻፺፪ ዘ፹ወ፩ዱ ፡ ሶበሰ ፡ ኢኮነ ፡ ሕግ ፡ ወፍልጠተ ፡ መዓርጋት ፡ ዘዘዚእሁ ፡ ዘተሠርዐ ፡ እምኮነ ፡ ይትለአክ ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረት ፡ በ፩ዱ ፡ ስም ፡ ዳእሙ ፡ ሶበ ፡ አእመርነ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ ጸዋትወ ፡ ግብር ፡ ፈለጥነ ፡ ለኤጲስቆጶሳት ፡ ይኩኑ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ወለቀሳውስት ፡ ክህነተ ፡ ወለዲያቆናት ፡ መልእክተ ፡ ምስሌሆሙ ። ወእለሰ ፡ ይዌልጡ ፡ መዓርጋተ ፡ አኮ ፡ ዘይትቃወሙ ፡ ኪያነ ፡ ዳእሙ ፡ ይትቃወምዎ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረት ፡ ወልደ ፡ እግዚእቤሔር ፡ ዐቢይ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡

፪፻፺፫ ራብዕ ፡ በእንተ ፡ ፪ቱ ፡ ፆታ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡



ገባውንም ፡ ትፈታዋለች ።

፪፻፺ ፴፪ ። ንጉሥን ፡ የሚቃወም ፡ ሰው ፡ ምንም ፡ ልጁ ፡ ወይም ፡ ወዳጁ ፡ ቢሆን ፡ ቅጣት ፡ የሚገባው ፡ ከሆነ ፡ ካህናትንማ ፡ የሚቃወም ፡ ሰው ፡ እንዴት ፡ የበለጠ ፡ ቅጣት ፡ አይገባውም ። ክህነት ፡ ከመንግሥት ፡ እንድትበልጥ ፡ እንደዚሁም ፡ ክህነትን ፡ የሚቃወም ፡ ሰው ፡ ቅጣት ፡ ንጉሥን ፡ ከሚቃወም ፡ ሰው ፡ ቅጣት ፡ ይበልጣል ። አቤሴሎምና ፡ አሚናዳብ ፡ ከቅጣት ፡ እንዳልዳኑ ፡ ከሁለቱ ፡ ቅጣት ፡ የሚድን ፡ አንድም ፡ የለም ። ቆሬ ፡ ዳታንና ፡ አቤሮንም ፡ እንዳልዳኑ ፡ እኒህ ፡ ዳዊት ፡ ንጉሥን ፡ ተቃውመውታልና ፡ እነዚህም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ ተቃውመዋቸዋልና ።

፪፻፺፩ ረሰጠጅ ፡ ፴፱ ። ሁሉም ፡ እያንዳንዱ ፡ በተሰጠው ፡ መዓርግ ፡ ይኑር ። ከእናንተ ፡ ወገን ፡ አንድስ ፡ እንኳ ፡ ያልተሰጠውን ፡ የባልንጀራውን ፡ መዓርግ ፡ አይቀማ ። ስለዚህ ፡ በቆሬና ፡ በዖዝያን ፡ አምሳል ፡ እግዚአብሔርን ፡ ታሳዝኑታላችሁ ። እነርሱ ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ የካህናትን ፡ መዓርግ ፡ ቀምተዋልና ፡ እኒህም ፡ በእሳት ፡ ተቃጠሉ ፡ ንጉሡም ፡ ፊቱ ፡ በለምጽ ፡ ነደደ ። እግዚአብሔር ፡ የተነጋገረው፡ ሙሴም ፡ የክህነትን ፡ ሹመት ፡ ይፈጽም ፡ ዘንድ ፡ የሚገባውን ፡ ወሰነ ። ከርሱም ፡ ወገን ፡ ካህን ፡ የሚሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ለያንዳንዱ ፡ የሚገባውን ፡ ለየ ። ለሌዋውያን ፡ የሚገባውንም ፡ አንድስ ፡ እንኳ ፡ ከተቀበላት ፡ አገልግሎቱ ፡ ወጥቶ ፡ የተደፋፈረ ፡ ቢኖር ፡ ቅጣቱ ፡ ሞት ፡ ነው ።

፪፻፺፪ ፹፩ ። ሕግ ፡ ባይኖር ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሆኖ ፡ የተሠራ ፡ የመዓርግ ፡ ልዩነትም ፡ ባይኖር ፡ ፍጥረቱ ፡ ሁሉ ፡ በአንድ ፡ ስም ፡ በተጠራ ፡ ነበር ። የሥራውን ፡ ስልት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ በአወቅን ፡ ለየን ፡ እንጂ ። ኤጲስቆጶሳት ፡ የካህናት ፡ አለቃ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ቀሳውስት ፡ ያስተምሩ ፡ ዘንድ ፡ ዲያቆናትም ፡ ከነርሱ ፡ ጋር ፡ ያገለግሉ ፡ ዘንድ ፡ ለየን ፡ እንጂ ። መዐርጋትን ፡ የሚለውጡ ፡ ግን ፡ እኛን ፡የሚቃወሙ ፡ አይደለም ። የፍጥረቱ ፡ ሁሉ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ የሆነውን ፡ ታላቁን ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ልጅ ይቃወሙታል ፡ እንጂ ።

፪፻፺፫ አራተኛው ፡ ስለ ፡ ሁለቱ ፡ ወገን ፡ ይናገራል ።

ዘይኤዝዝዎሙ ። በደስ ፡ ፳ወ፱ቱ ፡ ይቤ ፡ እግዚ እ ፡ "ሶበ ፡ ቦእክሙ ፡ ውስተ ፡ ቤት ፡ በሉ ፡ ሰላም ፡ ይኩን ፡ ለሰብእ ፡ ዝንቱ ፡ ቤት ። ወለ እመ ፡ ሀሎ ፡ ህየ ፡ ብእሴ ፡ ሰላም ፡ ሰላምክሙ ፡ ይኅድር ፡ ላዕሌሁ ፡ እመሰ ፡ ኢረከበ ፡ ዘይደ ልዎ ፡ ሰላምክሙ ፡ ይግባእ ፡ ኀቤክሙ" ። እመ ሰ ፡ ኮነ ፡ ሰላም ፡ ይገብእ ፡ ኀበ ፡ ዘፈነዎ ፡ ሶበ ፡ ኢረከበ ፡ ዘይደልዎ ። ወመርገምኒ ፡ ካዕበ ፡ ይት መየጥ ፡ ፈድፋደ ፡ ኀበ ፡ ርእሱ ፡ ለዘፈነዎ ፡ በዓ መፃ ። ወኵሉ ፡ ዘይረግም ፡ በከንቱ ፡ ረገመ ፡ ባሕቲቱ ፡ ነፍሶ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ሰሎሞን ፡ ከመ ፡ ያፍ ፡ ዘይሰርር ፡ ከማሁ ፡ መርገማት ፡ ፅሩዓት ፡ ኢይበጽሖ ፡ ላዕለ ፡ ፩ዱሂ ።

፪፻፺፬ በደስ ፡ ፴ወ፬ቱ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አው ፡ ቀሲስ ፡ አው ፡ ዲያቆን ፡ አው ፡ ዘቦቱ ፡ መዓርገ ፡ ክህነት ፡ ኢያርኩስ ፡ ልሳኖ ፡ በመር ገም ፡ ህየንተ ፡ በረከት ፡ ከመ ፡ ኢይረስ ፡ መር ገመ ፡ ህየንተ ፡ በረከት ። ወያእምር ፡ ኵሉ ፡ ለለ፩ዱ ፡ ምቅዋመ ፡ ዚአሁ ፡ ወይፈጽም ፡ ግብሮ በተማህሮ ፡ ወይኩኑ ፡ ኵሎሙ ፡ በ፩ዱ ፡ ሕሊና ፡ ወበ፩ዱ ፡ መንፈስ ።

፪፻፺፭ ሥርዋጽ ፡ ፺ቱ ፡ እንበረ ፡ ጴጥሮስ ፡ ዘ፳ወ፩ዱ ፡ ወኢያኅድግ ፡ ፩ዱሂ ፡ እምቀሳውስት ፡ ወዲያቆ ናት ፡ ጸሎቶ ፡ ወኢይፃእ ፡ ፍጡነ ፡ እምኔሃ ፡ ለነ ገረ ፡ ፩ዱሂ ፡ እምአይሁድ ፡ ወመምለክያነ ፡ ጣዖት ፡ ወዘገብረ ፡ ዘንተ ፡ ኢይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይትመየጥ ፡ ኀበ ፡ ምቅዋሙ ፡ ዘኮነ ፡ ውስቴቱ ፡ ቅዉመ ።

፪፻፺፮ ረስጣ ፡ ፺ወ፱ቱ ፡ ኢይትዐበይ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ላዕለ ፡ ቀሳውስት ፡ ወላዕለ ፡ ዲያቆናት ፡ ወኢይ ትዓበዩ ፡ ቀሳውስት ፡ ላዕለ ፡ ሕዝብ ፣ እስመ ፡ ቁመቱ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውእቱ ፡ በበይና ቲሆ ፡ ወሰእመ ፡ ኢሀለዉ ፡ ሕዝባውያን ፡ በላ ዕለ ፡ መኑ ፡ ይሠየሙ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ወቀሳው ስት ።

፪፻፺፯ መጅ ፡ ፫ቱ ፡ ወምግባረ ፡ ክህናት ፡ ሠናይት ፡ ትበቍዖሙ ፡ ለብዙኃን ፡ እስመ ፡ ውእቶሙ ፡ ይትሜሰሉ ፡ ባቲ ፡ ወከማሁ ፡ ካዕበ ፡ ኃጢአቶ ሙኒ ፡ ትሬስዮሙ ፡ ለሰብእ ፡ ሀካያነ ፡ እምሠና ያት ።

፪፻፺፰ ዶቅ ፡ ፳ወ፺ቱ ፡ ኢይደሉ ፡ ለካህናት ፡ አው ፡ ለሥዩማን ፡ ከመ ፡ ይንሥኡ ፡ አምጽዋታት ፡

ከነርሱ ፡ አንዱ ፡ የሚያዟቸው ፡ ነው ። በደስ ፡ ፳፱ ፡ ጌታችን ፡ "ወደ ፡ ቤት ፡ በገባችሁ ፡ ጊዜ ፡ ለዚህ ፡ ቤት ፡ ባለቤት ፡ ሰላም ፡ በሉ ፡ ከዚያ ፡ የሰላም ፡ ሰው ፡ ካለ ፡ ሰላማችሁ ፡ ይደርበት ፡ የሚገባው ፡ ሰው ፡ ባይገኝ ፡ ግን ፡ ሰላማችሁ ፡ ወደናንተ ፡ ይመለስ ፡ አለ ። (ማቴ ፡ ፲ ፡ ፲፩ -፲፫) ሰላም ፡ የሚቀበለው ፡ አጥቶ ፡ ወደ ፡ ባለቤቱ ፡ የሚመለስ ፡ ከሆነ ፡ መርገምም ፡ ደግሞ ፡ በማይ ገባ ፡ ወደ ፡ ረገመው ፡ ወደ ፡ ራሱ ፡ ይመለሳል ። በከንቱ ፡ የሚራገም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሰውነቱን ፡ ብቻ ፡ ረገመ ። ሰሎሞን ፡ ያፍ ፡ እንደሚበር ፡ እንዲሁም ፡ የማይገቡ ፡ መርገሞች ፡ በአንዱም ፡ ላይ ፡ አይደርሱም ፡ እንዳለ ፡ (ምሳ ፡ ፳፮ ፡ ፪) ።

፪፻፺፬ በደስ ፡ ፴፬ ፡ ስለዚህ ፡ የክህነት ፡ መዐርግ ፡ ያለው ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወይም ፡ ቄስ ፡ ወይም ፡ ዲያቆን ፡ ወይም ፡ የክህነት ፡ መዓርግ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ በበረከት ፡ ፈንታ ፡ አንደበቱን ፡ በመር ገም ፡ አያርክስ ፡ በበረከት ፡ ፈንታ ፡ መርገምን ፡ እንዳይወርስ ። አንዱም ፡ አንዱ ፡ መቋሚያውን ይወቅ ፡ ሥራውን ፡ በማስተማር ፡ ይፈጽም ፡ ሁሉም ፡ በአንድ ፡ አሳብና ፡ በአንድ ፡ ልብ ፡ ይሁኑ ።

፪፻፺፭ ሥርዋጽ ፡ ፺ ፡ ጴጥሮስ ፡ አዘዘ ፡ ፳፩ ፡ ከቀሳው ስት ፡ ከዲያቆናት ፡ ወገን ፡ አንዱስ ፡ እንኳ ፡ ጸሎቱን ፡ አይተው ፡ (አያቋርጥ) ፡ ጣዖትን ፡ ከሚ ያመልኩ ፡ ከአይሁድ ፡ ወገን ፡ ከአንዱ ፡ ጋር ፡ ለመነጋገር ፡ ከርሷ ፡ ፈጥኖ ፡ አይውጣ ፡ ይህን ፡ ያደረገ ፡ ቆሞበት ፡ ወደነበረው ፡ ወደመቋሚ ያው ፡ ይመለስ ፡ ዘንድ ፡ አይገባውም ።

፪፻፺፮ ረስጣ ፡ ፺፱ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በቀሳውስቱና ፡ በዲያ ቆናቱ ፡ ላይ ፡ አይታበይ ፡ ቀሳውስቱም ፡ በሕ ዝቡ ፡ ላይ ፡ አይታበዩ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አኗኗርዋ ፡ እርስ ፡ በርሷ ፡ በመከባበር ፡ ነውና ፡ ሕዝባውያንም ፡ ከሌሉ ፡ ኤጲስቆጶሳትና ፡ ቀሳ ውስት ፡ በማን ፡ ላይ ፡ ይሾማሉ ።

፪፻፺፯ መጅ ፡ ፫ ፡ የካህናት ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ብዙዎችን ፡ ትጠቅማቸዋለች ፡ እነርሱ ፡ በሷ ፡ ይመስሳሉና ፡ እንደዚሁም ፡ ደግመኛ ፡ ኃጢአታቸው ፡ ሰዎ ቹን ፡ ከበጎ ፡ ነገር ፡ እንዲሰንፉ ፡ ታደርጋቸዋለ ችና ።

፪፻፺፰ ዶቅ ፡ ፳፺ ፡ ካህናት ፡ ወይም ፡ ሹማምንት ፡ ምጽ ዋትን ፡ መቀበል ፡ አይገባቸውም ። በክህነት ፡

ከመ ፡ ኢይኩን ፡ ስላቅ ፡ ላዕለ ፡ መዓርገ ፡ ክህነት ፡ ወኢይደሉ ፡ ለ፩ዱሂ ፡ እምኔሆሙ ፡ ከመ ፡ ይክፍል ፡ ሰሎ ፡ መክፈልተ ፡ ወኢይንሣእ ፡ ክፍለ ፡ እምካልኡ ፡ ወኢይድሐዕ ፡ ከመ ፡ ይኩን ዝንቱ ፡ ካዕበ ፡ በውስቴቱ ፡ ወኢለካልአኒሆሙ ፡ ወኢይትፌሣሕ ፡ በዝንቱ ፡ ግብር ፡ ወኢይረስዮ ፡ ጽድቀ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘይደልዎሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ወዘይሜኒ ፡ በእንቲአሆሙ ፡ ከመ ፡ ኢይኩን ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ሕግ ፡ ነውር ፡ ለውሉደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

፩፻ ፺፱ ዘ፺ወ፱ቱ ፡ ኢይደልዎሙ ፡ ለካህናት ፡ ወለላእካነ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወለሊቃናተ ፡ ምእመናን ፡ ከመ ፡ ይርአዩ ፡ ምንተኒ ፡ እምርእየት ፡ ዘውስተ ፡ ከብካብ ፡ ወምሳሐት ፡ አላ ፡ ይትነሥኡ ፡ ወይሑሩ ፡ እምቅድመ ፡ ይባኡ ፡ መስተዘውዓን ።

፪፻ በይእቲ ፡ ፳ወ፩ዱ ፡ ወይትጋብኡ ፡ ኵሎሙ ፡ ጊዜ ፡ ንቅወተ ፡ ደርሆ ፡ ወይግበሩ ፡ ጸሎተ ፡ በመዝሙራት ፡ ወአንብቦ ፡ መጻሕፍት ፡ በከመ ፡ አዘዘ ፡ ሐዋርያ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ "ተመየጥ ፡ ኀበ ፡ አንብቦ ፡ እስከ ፡ እመጽእ" ። ወዘይደኀር ፡ እምሥዩማን ፡ ዘእንበለ ፡ ደዌ ፡ ወኢንጊደ ፡ ይትፈለጥ ። ወሰደውያንሂ ፡ ሐዊሮቶሙ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይከውኖሙ ፡ ፈውስ ፡ ለእመ ፡ ኢኮነ ፡ ደዌሆሙ ፡ ጽኑዕ ፡ ጥቀ ፡ ወስእሉሂ ፡ የሐውጽዎሙ ፡ ማእምራኒሆሙ ፡ እምሥዩማነ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ኵሎ ፡ ጊዜ ።

፪፻፩ በስ ፡ ፺ወ፰ቱ ፡ ወኢይንሣእ ፡ ፩ዱኒ ፡ እምሥዩማን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ርእየ ፡ ግሙራ ። ዘ፺ወ፱ቱ ፡ ወኢይምሐል ፡ ፩ዱ ፡ ውእቱ ፡ እምትእዛዛተ ፡ መጻሕፍት ። ዘ፻ ፡ ወኢይትመዓዕ ፡ ግሙራ ፡ አላ ፡ ይኩን ፡ ተዓጋሢ ። ዘ፻ወ፩ዱ ፡ ወኢይትናገር ፡ ላዕለ ፡ ፩ዱሂ ፡ በእኩይ ፡ እምቅድመ ፡ ይስማዕ ፡ ነገሮ ፡ እስመ ፡ ጽሑፍ ፡ ውእቱ ፡ ዘይብል ፡ ዘይተናገር ፡ ተናግሮ ፡ እምቅድመ ፡ ይስማዕ ፡ ዐብድ ፡ ውእቱ ፡ ወይከውኖ ፡ ነውረ ። ዘ፻ወ፪ቱ ፡ ወኢይኩን ፡ ገብረ ፡ ለአሐዱሂ ፡ እምሰብእ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘወሀቦሙ ፡ ግእዛነ ፡ ኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይመንንዎ ፡ ለግእዛኖሙ ፡ ወይኩኑ ፡ አግብርተ ፡ ለሰብእ ።

፪፻፪ ዘ፻ወ፫ቱ ፡ ወኢይኩኑ ፡ ግሙራ ፡ ዕቅፍተ ፡ ለሰብእ ፡ ከመ ፡ ኢይኩኑ ፡ ምክንያተ ፡ ለእኩየት ።



መዓርግ ፡ ላይ ፡ መዘባበት ፡ እንዳይሆን ፡ ክህነርስ ፡ ለአንዱስ ፡ እንኳ ፡ ድርሻውን ፡ ይክፍል ፡ ዘንድ ፡ አይገባውም ፡ ከባልንጀራው ፡ አብልጦ ፡ አይቀበል ። ዳግመኛም ፡ ይህ ፡ ስልጆቹ ፡ ለሌሎችም ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ እንዳይሰናከል ፡ በዚህ ፡ ሥራ ፡ ደስ ፡ አይበለው ። ለሕዝቡ ፡ ከሚገባቸው ፡ በቀር ፡ ትሩፋት ፡ አያስመስለው ፡ ስለነርሱም ፡ መልካም ፡ ወሬ ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ልጆች ፡ ነውር ፡ እንዳይሆን ።

፩፻ ፺፱ ፺፱ ፡ ካህናት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልጋዮች ፡ የምእመናን ፡ አለቆች ፡ ሠርግና ፡ ምሳ ፡ ከተዘጋጀበት ፡ ከማየት ፡ ወገን ፡ ምንምን ፡ ማየት ፡ አይገባቸውም ። ሚዘዝቶቹ ፡ ሳይገቡ ፡ አስቀድመው ፡ ተነሥተው ፡ ይሂዱ ፡ እንጂ ።

፪፻ በደስ ፡ ፳፩ ፡ ሁሉም ፡ ዶሮ ፡ በጮኸ ፡ ጊዜ ፡ ይሰብሰቡ ፡ በመዝሙርና ፡ መጻሕፍትን ፡ በማንበብ ፡ ጸሎት ፡ ያድርጉ ፡ ሐዋርያው ፡ "እስክመጣ ፡ ድረስ ፡ መጽሐፍን ፡ በማንበብ ፡ ኑር ፡ (፩ኛ ፡ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፲፫) ብሎ ፡ እንዳዘዘ ። ከሹማምት ፡ ወገን ፡ ሳይታመምና ፡ መንገድ ፡ ሳይሄድ ፡ ከጸሎት ፡ ማኅበር ፡ የሚቀር ፡ ይለይ ። ድውያንም ፡ ወደቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በመሄዳቸው ፡ ድኅነት ፡ ያገኛቸዋል ፡ ደዌያቸው ፡ እጅግ ፡ የጸና ፡ ካልሆነ ፡ አይቅሩ ። እነዚህንም ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሹማምንት ፡ ወገን ፡ የሚያውቋቸው ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ይጠይቋቸው ።

፪፻፩ በስ ፡ ፺፰ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሹማምት ፡ ወገን ፡ አንዱ ፡ ስንኳ ፡ ፈጽሞ ፡ አራጣ ፡ አይቀበል ። ፺፱ ፡ አንዱስ ፡ እንኳ ፡ መጻሕፍት ፡ ካዘዙት ፡ ወጥቶ ፡ አይማል ። ፻ ፡ ታጋሽ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ፈጽሞ ፡ አይቆጣ ። ፻፩ ፡ ነገሩን ፡ ከመስማቱ ፡ አስቀድሞ ፡ በአንዱም ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ አይናገር ። "ነገሩን ፡ ሳይሰማ ፡ አስቀድሞ ፡ የሚናገር ፡ ሰው ፡ ሰነፍ ፡ ነው ፡ ነውርም ፡ ይሆንበታል ።" (ምሳ ፡ ፲፰ ፡ ፲፫) ። የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ አለና ። ፻፪ ፡ ከሰው ፡ ወገን ፡ ለአንዱስ ፡ እንኳ ፡ ተገዥ ፡ አይሁን ፡ ነፃነቱን ፡ የሰጣቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ነውና ፡ ነፃነታቸውን ፡ ይንቋት ፡ ዘንድ ፡ ለሰውም ተገዦች ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ አይገባም ።

፪፻፪ ፻፫ ፡ የክፋት ፡ ምክንያት ፡ እንዳይሆኑ ፡ ለሰው ፡ ፈጽሞ ፡ እንቅፋት ፡ አይሁኑ ። ስለ ፡ ሥራችን ፡

እስመ ፡ ለእሙ ፡ ፀረፈ ፡ ፩ዱ ፡ ላዕለ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ በእንተ ፡ ምግባራቲነ ፡ ወይኤብሱ ፡ በርእየ ፡ ዚአነ ፡ ንሕነ ፡ ንከውን ፡ ምክንያተ ፡ ለዙሉ ፡ እከይ ። ዘ፳ወ፮ቱ ፡ ወኢየሐስዉ ፡ ግሙሬ ፡ ሥዩማነ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ። ዘ፸ ወ፪ቱ ፡ ወኢይጸልዩ ፡ ላዕለ ፡ አውስቦ ፡ ዳግ ማዊ ።

፻፶፫ ሥርዋጽ ፡ ፳ቱ ፡ ዘውእቱ ፡ ጸሎተ ፡ ተክሊል ፡ ወእኮ ፡ ጸሎተ ፡ ፍትሐት ።

፻፶፬ ዘ፸ወ፫ቱ ፡ ወኢይባእ ፡ ውስተ ፡ ጉባኤ ፡ አይ ሁድ ፡ አው ፡ ዘይመስሎ ፡ ዘ፸ወ፰ቱ ፡ ወኢይ ሑር ፡ ኀበ ፡ ማእደ ፡ ሐራ ፡ ጥቃ ፡ ወኢያፍቅድ ፡ ምንተኒ ።

፻፶፭ ዘ፹ወ፬ቱ ፡ ወእምከመ ፡ ሤጠ ፡ መነሂ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ጠቢበ ፡ ኢይግባእ ፡ ከመ ፡ ይግ ዝር ። ወለእመ ፡ ተሠይመ ፡ ፩ዱ ፡ እመ ፡ ኮነ ፡ ሀቀቤ ፡ ሥራይ ፡ ኢይትመየጥ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ምንተኒ ። ወእመኒ ፡ ኮነ ፡ ነሃቤ ፡ ብሩር ፡ አው ፡ ገባሬ ፡ ምስል ፡ ወኢይትመየጥ ፡ ከመ ፡ ይግ በር ፡ ሥዕለ ፡ ጣዖት ።

፻፶፮ ሥርዋጽ ፡ ፱ቱ ፡ ተናግረ ፡ እምድኅረ ፡ ቀኖና ፡ ዘተጽሕፈ ፡ ለነገሥታት ፡ ከመ ፡ ይዕቀቡ ፡ ካህ ናት ፡ ስብሐታተ ፡ ወጸሎተ ፡ ቍርባናት ፡ ወዘሰ ፡ ኢየአምር ፡ ያንብብ ፡ መጻሕፍተ ። ወካ ዕበ ፡ ይትዓቀቡ ፡ ካህናት ፡ እምተደምሮተ ፡ ብእሲት ፡ ዘማዊት ፡ እመኒ ፡ ምስለ ፡ ዘመዶሙ፡ አው ፡ ምስለ ፡ ነኪራት ፡ አላ ፡ ይኅሥሡ ፡ ዘማው ያነ ፡ በመጻሕፍተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ይት መየጡ ።

፻፶፯ ዘ፹ወ፯ቱ ፡ ወኢይኩን ፡ ሥዩመ ፡ ቤተ ፡ ክርስ ቲያን ፡ ለ፩ዱ ፡ መጋቢ ፡ ከመ ፡ ኢይርከቦ ፡ ኅዘን ፡ ወኢይኩን ፡ ኀፍረት ፡ በመዓርገ ፡ ክህ ነት ፡ እመንገሌሁ ፡ ወካልኣኒሁ ። ዘ፹ወ፩ዱ ፡ ወኢይንግዱ ፡ ግሙሬ ፡ አላ ፡ ይትመሀሩ ፡ ግብረ ፡ እደ ፡ በዘየሐይዉ ፡ በግብረ ፡ እደዊ ሆሙ ።

፻፶፰ ዘ፺ወ፪ቱ ፡ ወኵሉ ፡ ፍትሕ ፡ ዘተሠርዐ ፡ በእንተ ሥዩማነ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ኢይስድዎ ፡ ኀበ ፡ መኳንንተ ፡ ዓለም ፡ ዳእሙ ፡ ይስድዎ ፡ ኀበ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አው ፡ ኀበ ፡ ርእስ ፡ ቀሳውስት ፡ ከመ ፡ ይፍትሑ ፡ ቦቱ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ እኮ ፡ መኳ ንንተ ፡ ዓለም ፡ ዘይፈትሑ ፡ ላዕለ ፡ ቤተ ፡ ክርስ ቲያን ፡ አላ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትፈትሕ ፡



አንዱስ ፡ እንኳ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ቢሳ ደብ ፡ እኛን ፡ በማየት ፡ ይበድላሉና ፡ ለክፋት ፡ ሁሉ ፡ ምክንያት ፡ እንሆናለን ። ፳፮ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሹማምት ፡ ፈጽሞ ፡ አይዋሹ ። ፸፪ ፡ በሁለተኛ ፡ ጋብቻ ፡ ላይ ፡ አይጸልዩ ።

፻፶፫ ሥርዋጽ ፡ ፳ ፡ ይኸውም ፡ የፍትሐት ፡ ጸሎት ፡ ያይደለ ፡ የተክሊል ፡ ጸሎት ፡ ነው ።

፻፶፬ ፸፫ ፡ ወደ ፡ አይሁድ ፡ ጉባኤ ፡ ወይም ፡ ወደሚ መስለው ፡ አይግባ ። ፸፰ ፡ ወደ ፡ ሐራ ፡ ጥቃ ፡ ማዕድ ፡ አይሂድ ፡ ምንም ፡ አይፍቀድ ።

፻፶፭ ፹፬ ፡ ማንንም ፡ ከሾሙ ፡ ዘንድ ፡ ጥበበኛ ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ፡ እንገዝራለሁ ? አይበል ። አንዱስ እንኳ ፡ ቢሾም ፡ ሐኪም ፡ ቢሆን ፡ ምንምን ፡ ለመሥራት ፡ አይመለስ ። ብር ፡ አንጣሪ ፡ ወይም ፡ ምስል ፡ ሠሪ ፡ ቢሆን ፡ የጣዖት ፡ ሥዕል ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ አይመለስ ።

፻፶፮ ሥርዋጽ ፡ ፱ ፡ ለነገሥታት ፡ ከተጻፈው ፡ ሕግ ፡ በኋላ ፡ ተናገረ ። ካህናት ፡ ምስጋናዎችንና ፡ የቍርባኑን ፡ ጸሎት ፡ ያደርሱ ፡ ዘንድ ፡ የማያ ውቅ ፡ ግን ፡ መጻሕፍትን ፡ ያንብብ ፡ ዳግመ ኛም ፡ ካህናት ፡ ከዘማዊቱ ፡ ሴት ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ከመሆን ፡ ይጠበቁ ። ከዘመዶቻቸው ፡ ወይም ፡ ከባዕዶች ፡ ጋር ፡ ቢሆን ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ በእ ግዚአብሔር ፡ መጻሕፍት ፡ ዘማውያንን ፡ ይም ከሩ ፡ እንጂ ።

፻፶፯ ፹፯ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሹም ፡ ለአንዱስ ፡ እንኳ ፡ መጋቢ ፡ አይሁን ፡ ኀዘን ፡ እንዳያገኘው፡ ክርሱና ፡ ከባልንጀራዎቹ ፡ የተነሣ ፡ በክህነት ፡ መዓርግ ፡ ኀፍረትም ፡ እንዳይሆን ። ፹፩ ፡ ፈጽሞ ፡ አይነግዱ ፡ በእጃቸው ፡ ሥራ ፡ በሚጠ ቀሙ ፡ ገንዘብ ፡ ግብረ ፡ እድ ፡ ይማሩ ፡ እንጂ ።

፻፶፰ ፺፪ ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሹማምት ፡ የተ ሠራውን ፡ ፍርድ ፡ ሁሉ ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ ገዦች ፡ አይውሰዱት ፡ ወደ ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ይወስዱት ፡ እንጂ ። በርሱ ፡ ላይ ፡ ይፈርዱበት ፡ ዘንድ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ላይ ፡ የሚፈርዱ ፡ የዓለም፡ ገዦዎች ፡ አይደሉም ። ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሁ

ላዕለ ፡ ኵሎሙ ፡ ለለ፩፩ዱ ።

፫፻፱ ክፍል ፡ ዳግም ፡ በእንተ ፡ ትእዛዘ ፡ ሕዝብ ፡ ከመ ፡ ያክብሩ ፡ ካህናተ ፡ ወዘይደሉ ፡ ይትመሰልዎሙ ፡ ካህናት ፡ ወይግበርዎሙ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ቦቱ ።

፫፻፲ ድስቅ ፡ ፴ ፡ በከመ ፡ ባዕድ ፡ ዘኢኮነ ፡ ውእቱ ፡ እምሌዋውያን ፡ ኢይትከሀሎ ፡ ይፁር ፡ ምንተኒ ፡ አው ፡ ያብእ ፡ ምንተኒ ፡ ኀበ ፡ ምሥዋዕ ፡ ዘእንበለ ፡ ካህን ፡ ከማሁ ፡ አንትሙኒ ፡ ኢትግበሩ ፡ ምንተኒ ፡ ዘእንበለ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወእመ ፡ አኮሰ ፡ ይከውን ፡ ከንቶ ፡ ወኢይሤኒ ፡ ከመ ፡ ዖዝያን ፡ ወሳኦል ፡ ዘገብሩ ፡ ግብረ ፡ ክህነት ፡ እንዘ ፡ ኢይደልዎሙ ። ወአኮኑ ፡ ውእቱ ፡ ዖዝያን ፡ ካህን ፡ ዘኮነ ፡ ሥርግወ ፡ በለምጽ ፡ በእንተ ፡ ኃጢአቱ ። ወከማሁ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝባዊ ፡ ኢይደኅን ፡ እምኵነኔ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ መነኖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወተዐበየ ፡ ላዕለ ፡ ክህነት ፡ ወነሥአ ፡ ለሊሁ ፡ ክብረ ፡ በርእሱ ፡ ወኢተመሰሎ ፡ ለክርስቶስ ፡ ዘኢያንእደ ፡ ወኢሰብሐ ፡ ርእሶ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ዳእሙ ፡ ተፀንሖ ፡ እስከ ፡ ሰምዖ ፡ ለአብ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ "መሐለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢይኔስሕ ፡ ከመ ፡ አንተ ፡ ካህኑ ፡ ለዓለም ፡ በከመ ፡ ሢመቱ ፡ ለመልከ ፡ ጼዴቅ" ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘኢተሰብሐ ፡ ባሕቲቱ ፡ ዘእንበለ ፡ አቡሁ ፡ እንዘ ፡ ውእቱ ፡ ለሊሁ ፡ ምስሌሁ ፡ ወውእቱ ፡ ፩ዱ ፡ ምስሌሁ ፡ በኵሉ ፡ ግብር ፡ ወእፎ ፡ ይትከሀሎ ፡ ለ፩ዱ ፡ ከመ ፡ ይንሣእ ፡ ክህነተ ፡ ለርእሱ ፡ ዘእንበለ ፡ ይንሣእ ፡ ዘንተ ፡ መዓርገ ፡ እምዘይትሌዓል ፡ እምኔሁ ። ኢያውዐዮሙኑ ፡ እሳት ፡ ለደቂቀ ፡ ቆሬ ፡ እንዘ ፡ እሙንቱ ፡ ነገደ ፡ ሌዊ ፡ ሶበ ፡ ተቃወምዎሙ ፡ ለሙሴ ፡ ወአሮን ፡ ወገብሩ ፡ ዘኢይደሉ ፡ ሎሙ ።

፫፻፲፩ ውሰበሂ ፡ ኮኑ ፡ ዘይትለአኩ ፡ ለአጋንንት ፡ ይከብሩ ፡ እምሰብአሙ ፡ ወኢይፌጽሙ ፡ ምንተኒ ፡ እምግብሮሙ ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ሰላቅ ፡ ዘእንበለ ፡ ካህን ፡ ወይመስልዎሙ ፡ ከመ ፡ በሙ ፡ ልሳነ ፡ ለእልክቱ ፡ አእባን ፡ ወኵሎ ፡ ዘይአዝዝዎሙ ፡ ይሰምዕዎ ፡ ኪያሁ ፡ ወይገብሩ ፡ ወይሬእዩ ፡ ከመ ፡ ክቡሩ ፡ ክብርት ፡ ይእቲ ፡ ለማያት ፡



ላቸውም ፡ ላይ ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ትፈርዳለች ፡ እንጂ ።

፫፻፱ ክፍል ፡ ፪ ፡ ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ ትእዛዝ ፡ ካህናቱን ፡ ያከብሩ ፡ ዘንድ ፡ ካህናቱም ፡ ይመስሏቸው ፡ ዘንድ ፡ የሚገባውን ፡ ከነርሱም ፡ ጋር ፡ የሚያደርጉትን ፡ ይናገራል ።

፫፻፲ ድስቅ ፡ ፴ ፡ ከሌዋውያን ፡ ወገን ፡ ያይደለ ፡ ባዕድ ፡ ምንምን ፡ መሸከም ፡ እንደማይቻለው ፡ ወይም ፡ ከካህኑ ፡ በቀር ፡ ምንምን ፡ ወደቤተ ፡ መቅደሱ ፡ ያገባ ፡ ዘንድ ፡ እንደማይቻለው ፡ እናንተም ፡ እንደዚሁ ፡ ያለ ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ ፈቃድ ፡ ምንም ፡ አትሥሩ ። እንደዚህ ፡ ካልሆነ ፡ ግን ፡ ከንቱ ፡ ይሆናል ፡ አያምርም ፡ ሳይገባቸው ፡ የክህነትን ፡ ሥራ ፡ እንደሠሩ ፡ እንደ ፡ ዖዝያንና ፡ እንደ ፡ ሳኦል ፡ ዖዝያን ፡ ካህን ፡ ስለ ፡ ኃጢአቱ ፡ በለምጽ ፡ ዝንጕርጕር ፡ የሆነ ፡ አይደለምን ? እንደዚሁም ፡ ሕዝባዊ ፡ ሁሉ ፡ ከቅጣት ፡ አይድንም ፡ እርሱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ንቆታልና ፡ በክህነት ፡ ላይ ፡ ተደፋፍሮ ፡ ለራሱ ፡ ይህችን ፡ ክብር ፡ ተቀበለ ። ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ራሱን ፡ ፈጽሞ ፡ ያላመሰገነ ፡ ክርስቶስንም ፡ አልመሰለውም ። "እንደመልከጼዴቅ ፡ ሹመት ፡ የዓለም ፡ አገልጋይ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ ሲል ፡ እግዚአብሔር ፡ ማለ ፡ አልተመሰሰምም ፡ ሲል ፡ አብን ፡ እስኪሰማው ፡ ድረስ ፡ ታገሠ ፡ እንጂ ።" (ዕብ ፡ ፭ ፡ ፭ - ፮) ። ክርስቶስ ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ የተካከለ ፡ ሲሆን ፡ ያላባቱ ፡ ብቻውን ፡ ያልተመሰገነ ፡ ከሆነ ፡ እርሱም ፡ በሥራው ፡ ሁሉ ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ነው ። አንዱስ ፡ እንኳ ፡ ከርሱ ፡ ከሚበልጠው ፡ ይህንን ፡ መዓርግ ፡ ሳይቀበል ፡ ለራሱ ፡ ክህነትን ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ እንዴት ፡ ይቻለዋል ? እነርሱ ፡ የሌዊ ፡ ወገን ፡ ሲሆኑ ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ በተቃወሟቸው ፡ ጊዜ ፡ የማይገባቸውንም ፡ በሠሩ ፡ ጊዜ ፡ የቆሬን ፡ ልጆች ፡ እሳት ፡ አላቃጠለቻቸውምን ? ።

፫፻፲፩ አጋንንትን ፡ የሚያገለግሉ ፡ ከወገኖቻቸው ፡ የሚከብሩ ፡ ከሆነ ፡ ይኸችውም ፡ ሀበት ፡ ናት ፡ ከካህኑ ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ ሥራቸውን ፡ የማይጨርሱ ፡ ከሆነ ፡ እነዚህ ፡ ድንጋዮች ፡ አንደበት ፡ ያላቸው ፡ ይመስላቸዋል ። የሚያዝዟቸውን ፡ ሁሉ ፡ እሱን ፡ ይሰሙታል ። ይሠሩሉም ፡ ነፍስ ፡ የሌለው ፡ የማያት ፡ ክብሩ ፡ የከበረች ፡

ዘአልቦቱ ፡ ነፍስ ። አፎኬ ፡ ዘኢያደሉ ፡ ላዕሌነ ፡ ለነኒ ፡ እለ ፡ ብነ ፡ ሃይማኖት ፡ ብርሀት ፡ ወተ ሰፋ ፡ ጽድቅት ፡ ወጸኒሐ ፡ ዕሜት ፡ ዘለዓለም ፡ ዘምልእት ፡ ሰብሐተ ፡ እንበለ ፡ ፍርሃት ፡ ከመ ፡ ናክብሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላክነ ፡ ቅድመ ፡ ወእምዝ ፡ ለካህናቲሁ ፡ ወነሐሊ ፡ በእንተ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ከመ ፡ አሙንቱ ፡ አፉሁ ፡ ለእግ ዚአብሔር ።

፫፻፲፪ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ አሮን ፡ እኁወ ፡ ሙሴ ፡ ሶበ ፡ ረድአ ፡ ለሙሴ ፡ በነገር ፡ ተሰምየ ፡ ነቢየ ፡ ወተ ሰምየ ፡ ሙሴ ፡ አምላከ ፡ ለፈርዖን ፡ ዘውእቱ ፡ ንጉሥ ፡ ወሊቀ ፡ ካህናት ፡ ኅቡረ ፡ ከማክሙ ። ሰማዕክሙ ፡ በከመ ፡ ይቤሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሎቱ ፡ እነ ፡ ረሰይኩከ ፡ አምላከ ፡ ለፈርዖን ፡ ወአሮን ፡ እኁከ ፡ ይኩን ፡ ለከ ፡ ነቢየ ፡ ለምን ትኬ ፡ አንትሙ ፡ ዘኢትሔልዩ ፡ ዓራቅያኒክሙ ፡ በእንተ ፡ ነገር ፡ ከመ ፡ አሙንቱ ፡ ነቢያት ፡ ወኢትትለአከዎሙ ፡ ከመ ፡ አግብርተ ፡ እግዚ አብሔር ። ወዲያቆንኒ ፡ ይእዜ ፡ ውእቱ ፡ ንቡር፡ ለክሙ ፡ በምቅዋመ ፡ አሮን ፡ ወኤጲስቆጶስኒ ፡ አምሳለ ፡ ሙሴ ። ወሶበ ፡ ኮነ ፡ ዘሰመዮ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ ወአንትሙኒ ፡ አክብርዎ ፡ ካዕበ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ከመ ፡ አምላክ ፡ ወለዲያ ቆንኒ ፡ በአምሳለ ፡ ነቢይ ፡ ውእቱ ፡ ሎቱ ።

፫፻፲፫ ዘኒቱ ፡ ወዘይትናገር ፡ ቃለ ፡ ኅሡመ ፡ ላዕለ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ናሁ ፡ አበሰ ፡ ላዕለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢሰማዕክሙኑ ፡ ዘይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢትት ናገሩ ፡ ነገረ ፡ እኩየ ፡ ላዕለ ፡ አማልክት ። ወኢይ ምሰልክ ፡ ዝንቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ዘተብህለ ፡ በእንተ ፡ ጣዖታት ፡ አላ ፡ በእንተ ፡ ካህናት ፡ ወፈታሕት ፡ ዘተብህለ ፡ በእንቲአሆሙ ፡ “አማልክት ፡ አን ትሙ ፡ ወደቂቀ ፡ ልዑል ፡ ኵልክሙ ፡ ትሰመዩ” ወካዕበ ፡ ይቤሎሙ ፡ ሙሴ ፡ ለሕዝብ ፡ እለ ፡ ተቃወምዎ ፡ ሎቱ ፡ አኮ ፡ ላዕሌየ ፡ ዘታንጐረ ጕሩ ፡ አላ ፡ ላዕለ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ። ወሶበ ፡ ኮነ ፡ ዘይቤሎ ፡ ለሕዝባዊ ፡ እ ፡ ስሱዕ ፡ አው ፡ ዐብድ ፡ ኢይድኅን ፡ እምኵነኔ ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ትዕይርት ፡ ይከውን ፡ ላዕለ ፡ ክርስቶስ ፡ ወአፎኬ ፡ ይከውን ፡ ቃለ ፡ ዘይቤ ፡ ላዕለ ፡ ኤጲስ ቆጶስ ፡ በአንብሮ ፡ እዴሁ ፡ ዘወሀበክሙ ፡ እግዚ አብሔር ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ።



እንደሆነች ፡ ያያሉ ። የተረዳች ፡ ሃይማኖት ፡ የከበረች ፡ አለኝታ ፡ ያለፍርሃት ፡ ምስጋናን ፡ የተመላች ፡ የዘለዓለም ፡ ዋጋ ፡ ደጅ ፡ ጥናት ፡ ያለን ፡ እኛማ ፡ አስቀድመን ፡ አምላካችንን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ቀጥሎ ፡ ካህናቱን ፡ ማክበር ፡ እንዴት ፡ አይገባንም ? እነርሱም ፡ የእግዚአብ ሔር ፡ አፍ ፡ እንደሆኑ ፡ ስለ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ እናስብ ።

፫፻፲፪ የሙሴ ፡ ወንድም ፡ አሮን ፡ ሙሴን ፡ በነገር ፡ በረዳው ፡ ጊዜ ፡ ነቢይ ፡ የተባለ ፡ ከሆነ ፡ ሙሴ ም ፡ የፈርዖን ፡ አምላክ ፡ ተባለ ፡ ይኸውም ፡ እንደናንተ ፡ በአንድነት ፡ ንጉሥ ፡ ሊቀ ፡ ካህ ናት ፡ የተባለው ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ እር ሱን ፡ እኔ ፡ የፈርዖን ፡ አምላክ ፡ አደረግሁህ ፡ እንዳለው ፡ ሰምታችኋል ፡ ወንድምህ ፡ አሮ ንም ፡ ለአንተ ፡ ነቢይ ፡ ይሁንህ ፤ ስለነገር ፡ የሚያስታርቋችሁ ፡ ነቢያት ፡ እንደሆኑ ፡ ስለምን አታስቡም ፤ የእግዚአብሔርም ፡ አገልጋዮች ፡ እንደመሆናቸው ፡ ለምን ፡ አታገለግሏቸውም ? ዲያቆኑም ፡ ዛሬ ፡ በአሮን ፡ ቦታ ፡ አለላችሁ ። ኤጲስቆጶሱም ፡ በሙሴ ፡ አምሳል ፡ እግዚአብ ሔር ፡ አምላክ ፡ ብሎ ፡ የጠራው ፡ ከሆነ ፡ እና ንተም ፡ ዳግመኛ ፡ ኤጲስቆጶሱን ፡ እንደ ፡ አም ላክ ፡ ዲያቆኑንም ፡ በነቢዩ ፡ አምሳል ፡ አክብ ሩት ።

፫፻፲፫ ፯ ፤ በኤጲስቆጶሱ ፡ ላይ ፡ ከፉ ፡ ቃል ፡ የሚናገር፡ እነሆ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በደለ ። እግዚአብሔር በአማልክት ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አትናገሩ ፡ ያለውን ፡ አልሰማችሁምን ? ስለ ፡ ጣዖታቱ ፡ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ የተባለ ፡ አይምሰልህ ። ስለካህ ናትና ፡ ስለዳኞች ፡ ስለእነርሱ ፡ የተባለ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ “እናንተም ፡ ሁላችሁ ፡ አማልክትና ፡ የልዑል ፡ ልጆች ፡ ትባላላችሁ” ። (መዝ ፡ ፹፩ ፡ ፮) ። ዳግመኛም ፡ ሙሴ ፡ የሚቋቋሙትን ፡ ሕዝብ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ የምታንጐራጕሩ ፡ አይደላ ችሁም ፤ በእግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ላይ ፡ ታን ጐራጕራላችሁ ፡ እንጂ ። (ዘኊል ፡ ፲፮ ፡ ፲፩) ። አላቸው ። ሕዝባዊውን ፡ (ጨዋውን) ፡ አንተ ፡ ስሱ ፡ ወይም ፡ አንተ  ሰነፍ ፡ የሚለው ፡ ከቅ ጣት ፡ የማይድን ፡ ከሆነ ፡ ይህ ፡ ተግዳሮት ፡ በክርስቶስ ፡ ላይ ፡ ነውና ፡ በአንብሮተ ፡ እድ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ በሰጣችሁ በኤጲስቆጶሱ ፡ ላይማ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ የተናገረ ፡

፫፻፲፬ ረስጣ ፡ ፲ወ፩ዱ ፡ ኦ ፡ ወልድየ ፡ ለዘነገረከ ፡
ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኮነከ ፡ ምክንያተ ፡
ለሕይወት ፡ አክብሮ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡
በኵሉ ፡ ኃይልከ ፡ እምሐፈ ፡ ገጽከ ፡ ወጸማ ፡
እደዊከ ። ወእምከመስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ናሁ ፡
ረሰየከ ፡ ድልወ ፡ ከመ ፡ ትንሣእ ፡ እምኔሁ ፡
መብልዐ ፡ መንፈሳዌ ፡ ወሥጋዌ ፡ ወሕይወተ ፡
ዘለዓለም ፡ ወእንተኒ ፡ ይደልወከ ፡ ከመ ፡ ተሀበ፡
ፈድፋደ ፡ መብልዐ ፡ ማሳኔ ፡ ወዘመናዌ ።
ወናሁ ፡ ተጽሕፈ ፡ ለነ ፡ ከመ ፡ ይደልዎ ፡ ዓስቡ፡
ለዘይትቀነይ ። ዓዲ ፡ ይቤ ፡ "ኢትፍፅም ፡
አፉሁ ፡ ለብዕራይ ፡ ሶበ ፡ ታከይድ ፡ እክለ" ።
ወእልቦ ፡ ፩ዱሂ ፡ ዘይተክል ፡ ወይነ ፡ ወኢይበ
ልዕ ፡ ፍሬሁ ።

፫፻፲፭ ድስቅ ፡ ፲ወ፩ዱ ፡ ወኢንኤዝዝ ፡ ምንተኒ ፡ ለ፩ዱ
እምሕዝባውያን ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ እምግብረ ፡
ክህነት ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ መጥዎ ፡ ቍርባን ፡
ወጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ ወአንብሮተ ፡ እድ ፡
ለሢመተ ፡ ክህነት ፡ ኢለዐቢይ ፡ ወኢለንኡስ ።

፫፻፲፮ ኃምስ ፡ በእንተ ፡ ዘይትኬነኑ ፡ ቦቱ ፡ ረስጣ ፡
፲ወ፰ቱ ፡ ጠስ ፡ ፲ወ፱ቱ ፡ ፴ወ፰ቱ ፡ ንኤዝዝ ፡
ከመ ፡ ኢይባእ ፡ ቀሲስ ፡ ወዲያቆን ፡ ውስተ ፡
ተሐብዮ ፡ ወኢአኀዝ ፡ እምውስተ ፡ ሰብአ ፡ መዓ
ርጋት ፡ ወዘተሀበለ ፡ ሳዕለ ፡ ዝንቱ ፡ ይትመተር ፡
እምክህነቱ ። ዘ፳ወ፪ቱ ፡ ዘ፳ወ፫ቱ ፡ እመቦ ፡
ካህን ፡ ዘተሐበየ ፡ ብእሲ ፡ ይትገነሥ ፡ እምቤተ፡
ክርስቲያን ።

፫፻፲፯ ዘ፳ወ፫ቱ ፡ ወእመቦ ፡ ካህን ፡ ዘሐጸወ ፡ ርእሶ ፡
ይትመተር ፡ እመዓርጊሁ ። ወእመቦ ፡ ምእ
መን ፡ ዘሐጸወ ፡ ርእሶ ፡ ይትፈለጥ ። ወከማሁ ፡
እንበሩ ፡ ጉባኤ ፡ ኒቅያ ፡ ዘ፳ ፡ እመቦ ፡ ዘሐጸወ ፡
ርእሶ ፡ እመ ፡ ኮነ ፡ ካህነ ፡ ይትመተር ፡ እመዓ
ጊሁ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ሕዝባዌ ፡ ኢይኩን ፡
ካህነ ። ወአፀፀት ፡ ካዕበ ፡ ቀኖና ፡ ሐዋርያት ።
በስ ፡ ፳ቱ ፡ ፳ወ፩ዱ ፡ ፳ወ፪ቱ ፡ ፳ወ፳ቱ ፡ ወዘሐ
ጸወ ፡ ርእሶ ፡ እመ ፡ ኮነ ፡ ካህነ ፡ ይትመተር ፡
ወይሰደድ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ፫ተ ፡
ዓመተ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ሕዝባዌ ፡ ይትፈለጥ ፡
፫ተ ፡ ዓመተ ።

፫፻፲፰ ዘ፳ወ፱ቱ ፡ ወካህን ፡ ዘአዝለፈ ፡ ተዋንዮ ፡ ቀር
ቂስ ፡ ለእመ ፡ ኢኀደገ ፡ ይትመተር ፡ እመዓር
ጊሁ ፡ ወከማሁ ፡ ኵሎሙ ፡ ምእመናን ። ዘ፺

እንዴት ፡ ይሆን ? ።

፫፻፲፬ ረስጣ ፡ ፲፩ ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ የእግዚአብሔርን ፡
ቃል ፡ የነገረህንና ፡ ለሕይወት ፡ ምክንያት ፡
የሆነህን ፡ ከፊትህ ፡ ላብና ፡ ከእጅህ ፡ ድካም ፡
ባገኘኸውና ፡ በኃይልህ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ አክብረው ፡ (ርዳው) ፡ እነሆ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ሥጋዊውንና ፡ መንፈሳዊውን ፡ ምግ
ብ ፡ የዘለዓለምን ፡ ሕይወት ፡ ከርሱ ፡ እንድትቀ
በል ፡ ዝግጁ ፡ ካደረገህ ። አንተም ፡ ፈጽሞ ፡
ጠፊውንና ፡ ዘመናዊውን ፡ ምግብ ፡ ትሰጠው ፡
ዘንድ ፡ ይገባሃል ። እነሆ ፡ ለሚያገለግል ፡ ዋጋ
ው ፡ እንደሚገባው ፡ ተጽፎልናል ። ዳግመኛም ፡
እህል ፡ በምታበራይበት ፡ ጊዜ ፡ የበሬውን ፡
አፍ ፡ አትለጉመው ፡ አለ ፡ አንዱስ ፡ እንኳ ፡
ወይን ፡ ተክሎ ፡ ፍሬውን ፡ የማይበላ ፡ የለም ።

፫፻፲፭ ድስቅ ፡ ፲፩፡ ከክህነት ፡ ሥራ ፡ ወገን ፡ ከሕዝባ
ውያን ፡ ወገን ፡ ለአንዱ ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡
ምንም ፡ እናዝዝም ። ይኸውም ፡ ሥጋውንና ፡
ደሙን ፡ ማቀበል ፡ የክርስትና ፡ ጥምቀት ፡ ማጥ
መቅ ፡ ለታላቅም ፡ ሆነ ፡ ለታናሽ ፡ ለክህነት ፡
ሹመት ፡ እጅን ፡ መጫን ፡ ነው ።

፫፻፲፮ እምስተኛ ፡ ስለሚቀጡበት ፡ ይናገራል ። ረስጣ
፲፰ ፡ ጠስ ፡ ፲፱ ፡ ፴፰ ፡ ቄስ ፡ ዲያቆንም ፡ መዓ
ርግ ፡ ካላቸው ፡ ሰዎች ፡ ወገን ፡ ዋስ ፡ ወይም ፡
ተያዥ ፡ እንዳይሆን ፡ እናዝዛለን ። ይህን ፡ የተ
ደፋፈረ ፡ ግን ፡ ከክህነቱ ፡ ይሻር ። ፳፪ ፡ ፳፫ ፡
ለሰው ፡ ዋስ ፡ የሆነ ፡ ካህን ፡ ቢኖር ፡ ከቤተ ፡
ክርስቲያን ፡ ''ለይ ።

፫፻፲፯ ፳፫ ፡ የራሱ... ...ል ፡ የሰለበ ፡ ካህን ፡ ቢኖር ፡
ከሹመቱ ፡ ይሻር ፡ የራሱንም ፡ አካል ፡ የሰለበ ፡
ምእመን ፡ ቢኖር ፡ ይለይ ። የኒቅያ ፡ ጉባኤም ፡
በ፳ኛው ፡ አንቀጽ ፡ እንደዚሁ ፡ አዝዞዋል ፤
የራሱን ፡ አካል ፡ የሰለበው ፡ ካህን ፡ ቢሆን ፡
ከሹመቱ ፡ ይሻር ። ሕዝባዊ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡
ካህን ፡ አይሁን ። ዳግመኛም ፡ የሐዋርያት ፡
ቀኖና ፡ አዝዛለች ። በሰ ፡ ፳ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪ ፡ ፳፳ ፡
የራሱን ፡ አካል ፡ የሰለበ ፡ ካህን ፡ ቢሆን ፡ ይሻር፡
ሦስት ፡ ዓመትም ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይለይ።
ሕዝባዊ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ይለይ።

፫፻፲፰ ፳፱ ፡ ገበጣ ፡ መጫወትን ፡ የሚያዘወትር ፡
ካህን ፡ መጫወቱን ፡ ባይተው ፡ ከሹመቱ ፡ ይሻ
ር። እንደዚሁም ፡ ምእመናን ፡ ሁሉ ። ፺፪ ፡ ካህ

ወ፱ቱ ፡ እመቦ ፡ ካህን ፡ አው ፡ ሕዝባዊ ፡ ዘሰሐቀ ፡ በበሃም ፡ አው ፡ በዕዉር ፡ አው ፡ በነዳይ ፡ አው ፡ በሐንካስ ፡ ይትፈለጥ ።

፫፻፲፱ ረስጠጅ ፡ ፳ወ፱ቱ ፡ ወዘተረክበ ፡ በዝሙት ፡ አው ፡ በሰርቅ ፡ አው ፡ በመሐላ ፡ ዘሐሰት ፡ ይትመተር ፡ እምክህነቱ ፡ ወኢይሰደድ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢይኴንን ፡ በ፩ዱ ፡ አበሳ ፡ ፪ተ ፡ ጊዜያተ ።

፫፻፳ ዘ፵ተ፯ቱ ፡ ወዘተግኅሠ ፡ እምአውሰበ ፡ ወበሊዐ ፡ ሥጋ ፡ ወሰትየ ፡ ወይን ፡ እንዘ ፡ ይሔሊ ፡ ከመ ፡ ርኩሳን ፡ እሙንቱ ፡ ወሕሩማን ፡ ሎቱ ፡ ወዘረስየ ፡ ርእሶ ፡ ዘይኄይስ ፡ እምቢጹ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ይትመተር ፡ እመሰ ፡ ኀደገ ፡ ዘንተ ፡ በእንተ ፡ ፍኖተ ፡ ተፀምዶ ፡ ወምንኵስና ፡ ወተቀንየ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብውሕ ፡ ዘ፵ወ፱ቱ ፡ ወለእመ ፡ በልዐ ፡ በቤተ ፡ ምዝፋናት ፡ ወሰትየ ፡ በማኅደረ ፡ ዘማውያን ፡ ይሰደድ ። ዘ፶ወ፬ቱ ፡ አው ፡ በልዐ ፡ ማውታ ፡ አው ፡ ብላዐ ፡ አርዌ ፡ ይፃእ ። ወከማሁ ፡ ኵሉ ፡ ዘይበውእ ፡ ምኵራበ ፡ አይሁድ ፡ ለጸልዮ ፡ ወቤተ ፡ ሐራ ፡ ጥቃ ፡ ለረኪበ ፡ ፈውስ ፡ ባቲ ፡ ይትመተር ፡ ወይሰደድ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያን ።

፫፻፳፩ ዘ፷ወ፺ቱ ፡ ወከማሁ ፡ ኵሉ ፡ ዘይጸውም ፡ ምስለ ፡ አይሁድ ፡ ወይገብር ፡ በዓለ ፡ ምስሌሆሙ ፡ አው ፡ ነሥአ ፡ እምኔሆሙ ፡ ክብረ ፡ በዓላቲሆሙ ፡ ዘከመ ፡ ናእት ፡ ወዘይመስሎ ፡ እመ ፡ ኮነ ፡ ካህነ ፡ ይትመተር ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ እምሕዝብ ፡ ይትፈለጥ ። ዘ፸ወ፩ቱ ፡ ወከማሁ ፡ እመ ፡ ፈነወ ፡ ኀበ ፡ ምኵራበ ፡ አይሁድ ፡ አው ፡ ኀበ ፡ መካናቲሆሙ ፡ ለኢምእመናን ፡ አው ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናቲሆሙ ፡ ለሐራ ፡ ጥቃ ፡ አምኃ ፡ ይሰደድ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ለእግዚአብሔር ።

፫፻፳፪ ረስጠጅ ፡ ፸ወ፯ቱ ፡ ወኵሉ ፡ ዘኢይጸውም ፡ ጾመ ፡ ፵ ፡ አው ፡ ጾመ ፡ ረቡዕ ፡ ወዓርብ ፡ ዘእንበለ ፡ ይክልአ ፡ ሕማም ፡ ሥጋዊ ፡ ይትመተር ።

፫፻፳፫ ረስጠጅ ፡ ፩ዱ ፡ በስ ፡ ፵ወ፫ቱ ፡ እመቦ ፡ ካህን ፡ ዘአውሰበ ፡ እምድኅረ ፡ ነሢአቱ ፡ መዓርገ ፡ ክህነት ፡ ይትመተር ፡ እመዓርጊሁ ፡ ይትዓወቅ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አው ፡ ቀሲስ ።

፫፻፳፬ ዘ፵ወ፬ቱ ፡ ወለእመ ፡ አገበርዎ ፡ ለ፩ዱ ፡ እምሥዩማነ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከመ ፡ ይስተይ ፡



ን ፡ ወይም ፡ ሕዝባዊ ፡ በዲዳ ፡ ወይም ፡ በዕዉር ፡ ወይም ፡ በአንድ ፡ ዓይና ፡ ወይም ፡ በአንካሳ ፡ የሳቀ ፡ ቢኖር ፡ ይለይ ።

፫፻፲፱ ረስጠጅ ፡ ፳፱ ፡ በዝሙት ፡ ወይም ፡ በሥርቆት ፡ ወይም ፡ በሐሰት ፡ በመማል ፡ የተገኘ ፡ ከክህነቱ ፡ ይሻር ። ከምእመናን ፡ ግን ፡ አይለይ ። እግዚአብሔር ፡ በአንድ ፡ በደል ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ አይቀጣምና ።

፫፻፳ ፵፯ ፡ ከጋብቻ ፡ ሥጋን ፡ ከመብላት ፡ ወይንን ፡ ከመጠጣት ፡ እነርሱ ፡ ርኩሳን ፡ ናቸው ፡ የተከለከሉም ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ በማሰብ ፡ የራቀ ፡ ራሱንም ፡ ከባልንጀራው ፡ የሚበልጥ ፡ ያደረገ ፡ ቢኖር ፡ ስለዚህ ፡ ይሻር ። ስለ ፡ ምንኵስናና ፡ ስለ ፡ ተባሕትዎ ፡ ሕግ ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ስለመገዛት ፡ ይህን ፡ ቢተው ፡ ግን ፡ ይገባዋል ። ፵፱ ፡ በመዝፈኛዎች ፡ ቤት ፡ ቢበላ ፡ በዘማውያንም ፡ ማደሪያ ፡ ቢጠጣ ፡ ይለይ ። ፶፬ ፡ የሞተውን ፡ ወይም ፡ የአውሬውን ፡ ትራፊ ፡ የበላ ፡ ይለይ ። እንደዚሁም ፡ ለመጸለይ ፡ ወደ ፡ አይሁድ ፡ ምኵራብ ፥ በርስዋ ፡ ደኅንነትን ፡ ለማግኘት ወደ ፡ ሐራ ፡ ጥቃ ፡ ቤት ፡ የሚገባ ፡ ሁሉ ፡ ይሻር ። ከቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ይለይ ።

፫፻፳፩ ፷፺ ፡ እንደዚሁ ፡ ከአይሁድ ፡ ጋር ፡ የሚጾም ፡ ከነርሱም ፡ ጋር ፡ በዓል ፡ የሚያደርግ ፡ ወይም ፡ ከእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ለክብረ ፡ በዓላቸው ፡ እንደ ፡ ቂጣ ፡ ያለውን ፡ የሚመስለውንም ፡ የተቀበለ ፡ ሁሉ ፡ ካህን ፡ ቢሆን ፡ ይሻር ፡ ከሕዝቡ ፡ ወገን ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ይለይ ። ፸፩ ፡ እንደዚሁም ፡ ወደ ፡ አይሁድ ፡ ምኵራብ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ አሳመኑ ፡ ሰዎች ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሐራ ፡ ጥቃ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ቢልክ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይለይ ።

፫፻፳፪ ረስጠጅ ፡ ፸፯ ፡ ሥጋዊ ፡ ሕማም ፡ ሳይከለክለው ፡ ጾመ ፡ አርብዓን ፡ ወይም ፡ የዓርብንና የረቡዕን ፡ ጾም ፡ የማይጾም ፡ ይሻር ።

፫፻፳፫ ረስጠጅ ፡ ፩ ፡ በስ ፡ ፵፫ ፡ የክህነትን ፡ መዓርግ ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ ያገባ ፡ ካህን ፡ ቢኖር ፡ ከሹመቱ ፡ ይሻር ። ኤጲስቆጶስ ፡ ወይም ፡ ቄስ ፡ እንደሆነ ፡ ይታወቃል ።

፫፻፳፬ ፵፬ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሹማምት ፡ ወገን ፡ አንዱን ፡ በመዓልት ፡ ይጠጣ ፡ ዘንድ ፡ ግድ ፡

አንቀጽ ፡ ፱ ።

በመዓልት ፡ ይትዓቀብ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡ አው ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ ዘሰትየ ፡ ቦቱ ፡ ወኢይፃእ ፡ እምኔሁ ፡ ግሙራ ፡ ከመ ፡ ኢይኩን ፡ ዕቅፍተ ፡ ለሕዝብ ። ወለእመ ፡ ሰትየ ፡ ቀሲስ ፡ ወሰከረ ፡ ወተዓርቀ ፡ ይፃእ ፡ ፯ተ ፡ ሱባዔያተ ፡ ወይንበር ፡ ፩ደ ፡ ዓመተ ፡ በመዓርግ ፡ ዘይቴሐት ፡ እምኔሁ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ አስተኀፈረ ፡ ዘንተ ፡ መዓርገ ፡ ዐቢየ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዲያቆነ ፡ ይፃእ ፡ ፭ተ ፡ ሱባዔያተ ፡ ወይንበር ፡ ፩ደ ፡ ወርኀ ፡ እንዘ ፡ ይትለአክ ፡ ለሥዩማን ፡ በአምሳለ ፡ ንፍቀ ፡ ዲያቆን ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ አናጕንስጢስ ፡ አው ፡ ዐጻዌ ፡ አንቀጽ ፡ ይጸኡ ፡ ፫ተ ፡ ሱባዔያተ ፡ ወይቅሥፍዎሙ ፡ ፵ ፡ ጊዜያተ ፡ ዘእንበለ ፡ አሐቲ ፡ በትእዛዘ ፡ ቀሲስ ።

፫፻፹፭ ዘ፺ወ፯ቱ ፡ ወኢይትናገር ፡ ፩ዱ ፡ እምሥዩማነ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ምንተኒ ፡ ነገረ ፡ ነፍረት ፡ ኢማእከለ ፡ ሥዩማን ፡ ወኢማእከለ ፡ ሕዝባውያን ፡ ወኢይሳለቅ ፡ ላዕለ ፡ መኑሂ ፡ እምሰብእ ፡ እለ ፡ ቦሙ ፡ ነውር ፡ በሥጋሆሙ ፡ ወኢይትዐየር ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ አ ፡ ዕዉር ፡ አ ፡ ጽሙም ፡ አ ፡ ሐጉጽ ፡ አ ፡ ገብር ፡ አ ፡ ዐጋማዊ ፡ አ ፡ ሀካይ ፡ አ ፡ ሰዱድ ፡ ወዘተርፉ ፡ ትዕይርታት ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ከመዝ ፡ ይጼእል ፡ ሰብአ ፡ ሥጋዌ ፡ ይገሥጽዎ ፡ በአምሳለ ፡ ሕፃን ፡ ንኡስ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘተሠይመ ፡ በኊልቈ ፡ ካህናት ፡ ይሰደድ ፡ እስከ ፡ ይትፌጸም ፡ ፍትሐ ፡ ኵነኔ ።

፫፻፹፮ ዘ፺ወ፱ቱ ፡ እመቦ ፡ ዘኮነ ፡ ሰምዐ ፡ በሐሰት ፡ ላዕለ ፡ ፩ዱሂ ፡ ከመ ፡ ይሠዐር ፡ እምሢመቱ ፡ አው ፡ ከመ ፡ ይትኰነን ፡ ይደልዎ ፡ ኵነኔ ፡ ዝኩ ፡ ዘኮነ ፡ ሰምዐ ፡ በሐሰት ፡ ላዕሌሁ ።

፫፻፹፯ ዘ፻ወ፩ዱ ፡ ወለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ፩ዱሂ ፡ ከመ ፡ ይድኀር ፡ ብእሲቶ ፡ ወጸሐፈ ፡ ፩ዱ ፡ እምካህናት ፡ መጽሐፈ ፡ ኅዳጋቲሃ ፡ ይሰደድ ፡ እስከ ፡ ይመይጦ ፡ ለተዋስቦ ፡ ወያስተሳልሞ ።

፫፻፹፰ ዘ፻ወ፪ቱ ፡ ወለእመ ፡ ሀሎ ፡ ፩ዱሂ ፡ ዘያበዝኀ ፡ አስተዋድዮ ፡ ማእከለ ፡ ሥዩማን ፡ ይኅድግ ፡ ምስሌ ፡ ወካዕበ ፡ ወለእመ ፡ አዝለፈ ፡ ወኢኀደገ ፡ ይረድ ፡ እመዓርጊሁ ፡ እስከ ፡ ይትከላእ ፡ ወእመሰ ፡ ኢኀደገ ፡ ይሰደድ ።

ስለ ፡ ካህናት ፡ ሁሉ ።

ቢሉት ፡ ከቤቱ ፡ ወይም ፡ ከጠጣበት ፡ ቦታ ፡ ይቀመጥ ። ለሕዝቡ ፡ መሰናክል ፡ እንዳይሆን ፡ ፈጽሞ ፡ ከርሱ ፡ አይውጣ ፡ ቄስ ፡ ጠጥቶ ፡ ቢሰክር ፡ ቢራቆትም ፡ ሰባት ፡ ሱባዔ ፡ ይለይ ። በዝቅተኛ ፡ መዓርግ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ይቀመጥ ። እርሱ ፡ ይህን ፡ ታላቅ ፡ መዓርግ ፡ አዋርዷልና። ዲያቆን ፡ ቢሆን ፡ አምስት ፡ ሱባዔ ፡ ይለይ ፡ በንፍቀ ፡ ዲያቆኑ ፡ አምሳል ፡ ለሹማምቱ ፡ እያገለገለ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ይቀመጥ ። አናጕንስጢስ ፡ ወይም ፡ ዐፃዌ ፡ ኆኅት ፡ ቢሆኑ ፡ ሦስት ፡ ሱባዔ ፡ ይለዩ ። በቄሱ ፡ ትእዛዝ ፡ አንዲት ፡ ሳትቀር ፡ አርባ ፡ ጊዜ ፡ ይግረፏቸው ።

፫፻፹፭ ፺፯ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሹማምት ፡ ወገን ፡ አንዱስ ፡ እንኳ ፡ በሹማምቱ ፡ መካከልና ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ በማንም ፡ ላይ ፡ ማናቸውንም ፡ የሚያሳፍር ፡ ነገር ፡ አይናገር ። በሥጋቸው ፡ ነውር ፡ ካለባቸው ፡ ሰዎች ፡ ወገን ፡ በማንም ፡ ላይ ፡ አይዘብት ፡ አንተ ፡ ዕዉር ፡ አንተ ፡ ደንቆሮ ፡ አንተ ፡ ጕደሎ ፡ አንተ ፡ ባሪያ ፡ አንተ ፡ ግራኝ ፡ አንተ ፡ ለንፍ ፡ አንተ ፡ ስደተኛ ፡ እያለና ፡ የቀሩትንም ፡ ተግዳሮቶች ፡ በመናገር ፡ አይገዳደር ። ሥጋዊ ፡ ሰውን ፡ እንዲህ ፡ የሚሰድብ ፡ ከሆነ ፡ በትንሽ ፡ ልጅ ፡ አምሳል ፡ ይገሥፁት ። በካህናት ፡ ቁጥር ፡ ገብቶ ፡ የተሾመ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ የቅጣቱ ፡ ፍርድ ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ይለይ ።

፫፻፹፮ ፺፱ ፡ ከሹመቱ ፡ ይሻር ፡ ዘንድ ፡ ወይም ፡ ይቀጣ ዘንድ ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ በሐሰት ፡ የመሰከረ ፡ ቢኖር ፡ በሐሰት ፡ የመሰከረበት ፡ ሰው ፡ ይቀጣበት ፡ በነበረው ፡ መቀጫ ፡ ሊቀጣ ፡ ይገባዋል ።

፫፻፹፯ ፻፩ ፡ አንዱስ ፡ እንኳ ፡ ሚስቱን ፡ ሊፈታ ፡ ቢወድ ፡ ከካህናት ፡ ወገን ፡ አንዱም ፡ የምትፈታበትን ፡ ደብዳቤ ፡ ቢጽፍ ፡ ሊጋብቻ ፡ እስኪመልሰውና ፡ እስኪያስታርቀው ፡ ድረስ ፡ ይለይ ።

፫፻፹፰ ፻፪ ፡ በሹማምት ፡ መካከል ፡ አንዱስ ፡ እንኳ ፡ ነገር ፡ ሥራ ፡ የሚያበዛ ፡ ቢኖር ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይተው ። ቢያዘወትር ፡ ባይተው ፡ እስኪተው ፡ ድረስ ፡ ከሹመቱ ፡ ይሻር ። ባይተው ፡ ግን ፡ ይለይ ።

አንቀጽ ፡ ፱ ።

፻፶፱ ዘ፸ወ፱ቱ ፡ እመቦ ፡ እምካህናት ፡ ዘሰሐተ ፡ በጊዜ ፡ ቅዳሴ ፡ ኮንኤሁ ፡ ፩ዱ ፡ ሱባዔ ።

፻፷ ዘ፹ ፡ እመቦ ፡ እምሥዩማን ፡ ዘተቀጽለ ፡ አክሊለ ፡ ላዕለ ፡ ርእሱ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ቀሲሰ ፡ ይቁም ፡ በእፍኦ ፡ ፬ተ ፡ አውራኀ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዲያቆን ፡ ፪ተ ፡ አውራኀ ፡ ወእለ ፡ ተርፉሰ ፡ ይትኮነኑ ፡ እምኀበ ፡ ቀሳውስት ።

፻፷፩ ዘ፹ወ፩ዱ ፡ ወእመቦ ፡ እምካህናት ፡ ዘይነብብ ፡ ወይከሕድ ፡ ይኅድግ ፡ ወእመ ፡ አኮ ፡ ይሰደድ ፡ ከመ ፡ ኢይትኀጐሉ ፡ ሕዝብ ፡ በምክንያተ ፡ ዚአሁ ፡ በጊዜ ፡ ነጸርዎ ፡ እንዘ ፡ ውእቱ ፡ ኢግሁዕ ፡ ወዘኢይእኅዝ ፡ ልሳነ ፡ ዚአሁ ።

፻፷፪ ዘ፹ወ፪ቱ ፡ ወለእመ ፡ መሐለ ፡ ሥዩም ፡ መሐላ፡ በሃይማኖት ፡ ዘኢትደሉ ፡ እው ፡ ዕራቀ ፡ ይትኰንን ፡ እስከ ፡ ይትጌሠጽ ፡ ወዘተሀበለ ፡ ወመሐለ ፡ እንበለ ፡ እኪዜ ፡ ዘሉ ፡ በጽድቅ ፡ ፈጣሪ ፡ ክርስቶስ ፡ ወይቤ ፡ በዘፈጠሮ ፡ ለክርስቶስ ፡ እመ ፡ ኮነ ፡ ሕዝባዌ ፡ ይሰደድ ፡ አፍአ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ካህነ ፡ ይትመተር ፡ ወይክልእዎ ፡ እምተመጥዎ ፡ ምሥጢራት ። ዘ፶ወ፱ቱ ፡ ወኢይምሐል ፡ በዘኢተረክበ ፡ እምትእዛዛተ ፡ መጻሕፍት ።

፻፷፫ ዘ፺ ፡ ወለእመ ፡ ተቃወሞ ፡ ዲያቆን ፡ ለቀሲስ ፡ ይኰን ፡ ኮንኤሁ ፡ እምኀበ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እስከ ፡ ፯ቱ ፡ ሱባዔያት ። ወቀሲስኒ ፡ እመ ፡ መነኖ ፡ ይደልዎ ፡ ኮንኔ ፡ ዘተገብረ ፡ በዲያቆን ። ወአናጕንስጢስኒ ፡ ሶበ ፡ ተቃወሞ ፡ ስቀሲስ ፡ አው ፡ ለእመ ፡ ኢተአዘዘ ፡ ሎቱ ፡ ቦቱኒ ፡ ሥልጣን ፡ ለቀሲስ ፡ ከመ ፡ ይኰንኖ ፡ ዘእንበለ ፡ ትእዛዘ ፡ ኤጲስቆጶስ ።

፻፷፬ ዘ፺ወ፩ዱ ፡ ወለእመ ፡ ተጸልአ ፡ ካህን ፡ ምስለ ፡ ካህን ፡ ሱታፌሁ ፡ ይስደዱ ፡ ፪ኤሆሙ ፡ እስከ ፡ ይግብሩ ፡ ዕርቀ ፡ ወሰላመ ። ወሶበ ፡ ነጸሮ ፡ ሥዩም ፡ ለሱታፌሁ ፡ ሥዩም ፡ ይፃእ ፡ ከመ ፡ ይትራከቦ ፡ በሰላም ።

፻፷፭ ጴጥ ፡ ፹ወ፭ዱ ፡ ወኢይትለአክ ፡ ውስተ ፡ ምሥዋዐ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘለምጽ ፡ አኮ ፡ ክዊኖ ፡ ርኩሰ ፡ እስመ ፡ ኢኮነ ፡ ርኩሰ ፡ እምድኅረ ፡ ተወከፈ ፡ ጥምቀተ ፡ አላ ፡ ከመ ፡ ኢያጽእል ፡ ካህናተ ፡ እግዚእብሔር ፡ ወከማሁ ፡ ፍትሑ ፡ በእንተ ፡ ዝልጉስ ፡ ካዕበ ፡ እስመ ፡ ኢይደሉ ፡ ለዝልጉስ ፡ አመልእክተ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ።

ስለ ፡ ካህናት ፡ ሁሉ ።

፻፶፱ ፸፱ ፡ በቅዳሴ ፡ ጊዜ ፡ ከካህናት ፡ ወገን ፡ የሳቀ ፡ ቢኖር ፡ ቅጣቱ ፡ አንድ ፡ ሱባዔ ፡ ነው ።

፻፷ ፹ ፡ ከሹማምት ፡ ወገን ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ አክሊል፡ የተቀዳጀ ፡ ቢኖር ፡ ቄስ ፡ ቢሆን ፡ አራት ፡ ወር ፡ ዘውጭ ፡ ይቁም ፡ ዲያቆን ፡ ቢሆን ፡ ሁለት ፡ ወር ፡ ይቁም ። የቀሩት ፡ ግን ፡ ከቄስ ፡ ዘንድ ፡ ይቀጡ ።

፻፷፩ ፹፩ ፡ ከካህናቱ ፡ ወገን ፡ የሚናገርና ፡ የሚክድ ፡ ቢኖር ፡ ይተው ። ይህም ፡ ካልሆነ ፡ ይለይ ። እርሱ ፡ ያልተመከረ ፡ አንደበቱን ፡ ያልወሰነ ፡ ሁኖ ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ በርሱ ፡ ምክንያት ፡ ሕዝቡ፡ እንዳይጐዱ ።

፻፷፪ ፹፪ ፡ በማትገባ ፡ ወይም ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር፡ ባልተጠራባት ፡ ሃይማኖት ፡ መሐላ ፡ የማለ ፡ ሹም ፡ ቢኖር ፡ እስኪመከር ፡ ድረስ ፡ ይቀጣ ። በእውነት ፡ የሁሉ ፡ ፈጣሪ ፡ በሆነ ፡ በክርስቶስ፡ ሳይሆን ፡ የተደፋፈረና ፡ የማለ ፡ በክርስቶስ ፡ ፈጣሪም ፡ ብሎ ፡ የማለ ፡ ሰው ፡ ሕዝባዊ ፡ ቢሆን ፡ ይለይ ። ካህን ፡ ቢሆን ፡ ይሻር ፡ ሥጋ ውንና ፡ ደሙንም ፡ ከመቀበል ፡ ይከልክሉት ። ፶፱ ፡ ከመጻሕፍት ፡ ትእዛዝ ፡ ባልተገኘው ፡ አይማል ።

፻፷፫ ፺ ፡ ዲያቆን ፡ ቄሱን ፡ ቢቋቋመው ፡ ቅጣቱ ፡ ከኤጲስቆጶሱ ፡ ዘንድ ፡ እስከ ፡ ሰባት ፡ ሱባዔ ፡ ድረስ ፡ ይሁን ፡ ቄሱም ፡ ቢንቀው ፡ በዲያቆኑ ፡ የተደረገው ፡ ቅጣት ፡ ይገባዋል ። አናጕንስጢስም ፡ ቄሱን ፡ በተቃወመው ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ባይታዘዝለት ፡ ያለ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ትእዛዝ ፡ ይቀጣው ፡ ዘንድ ፡ ለቄሱ ፡ ሥልጣን ፡ አለው ።

፻፷፬ ፺፩ ፡ ካህን ፡ ከባልንጀራው ፡ ካህን ፡ ጋር ፡ ቢጣላ ፡ ዕርቅና ፡ ሰላምን ፡ እስኪያደርጉ ፡ ድረስ ፡ ሁለቱም ፡ ይለዩ ። ሹም ፡ ባልንጀራውን ፡ ሹም ፡ ባየው ፡ ጊዜ ፡ በሰላም ፡ ይገናኘው ፡ ዘንድ ፡ ይውጣ ።

፻፷፭ ጴጥ ፡ ፹፭ ፡ ለምጽ ፡ የያዘው ፡ ሰው ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ አያገልግል ። ርኩስ ፡ ሁኖ ፡ አይደለም ። ጥምቀትን ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ ርኩስ ፡ አይደለምና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ካህናት ፡ እንዳያበድብ ፡ ነው ፡ እንጂ ። ዳግመኛም ፡ የሥጋ ፡ ደዌ ፡ ለያዘው ፡ ፍርድ ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። የሥጋ ፡ ደዌ ፡ የያዘው ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማገልገል ፡ አይገባውምና ።

አንቀጽ ፡ ፱ ።

፫፻፴፯ ዶቅ ፡ ፵ወ፩ዱ ፡ ፵ወ፪ቱ ፡ ወኢይደሉ ፡ ለ፩ዱሂ ፡ እምካህናት ፡ ወመነኰሳት ፡ ወላእካነ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከመ ፡ ይሑር ፡ አመካኑ ፡ ኀበ ፡ መካነ ፡ ንግድ ። ባዕዳንሂ ፡ መነኰሳት ፡ ዘእንበለ ፡ አእምሮተ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወጸሎቱ ፡ ወትእዛዙ ፡ ወመጽሐፉ ፡ በጥያቄ ፡ ሃይማኖቱ ፡ ወሢመተ ፡ ክህነቱ ።

፫፻፴፰ ረስጠጅ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ወለእመ ፡ ኢሀሰወ ፡ ምስሌሁ ፡ ከታበ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘወሀቦ ፡ ክህነተ ፡ ኢይትወከፍዎ ፡ ውስተ ፡ ኍልቈ ፡ ካህናት ፡ ዘሂ ፡ ተወክፎ ፡ ይስደድ ፡ ምስሌሁ ፡ ወዘተስደ ፡ በግዘት ፡ ይኰንዲ ፡ ተስዶቱ ።

፫፻፴፱ ዘ፲ወ፩ዱ ፡ ወዘተናገረ ፡ ምስለ ፡ ውጉዝ ፡ አው ፡ ምስለ ፡ ስዱድ ፡ አው ፡ ጸለየ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ይስደድ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያን ።

፫፻፵ ክፍል ፡ ወኢይከውኖ ፡ ለ፩ዱኒ ፡ ከመ ፡ ይትዐቀፍ ፡ በእንተ ፡ ካህን ፡ ወኢ ፡ ከመ ፡ ይኩንኖ ፡ እንበለ ፡ ሊቁ ፡ ወመጽሐፍስ ፡ ይመርሕ ፡ እስመ ፡ ካህን ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ሠናየ ፡ በሑረቱ ፡ ኢይደሉ ፡ ኰንኖቱ ፡ ዘእንበለ ፡ አክብሮቱ ፡ ወተአገዞ ፡ ሎቱ ፡ በተሰናአዎ ። እመሰ ፡ ኮነ ፡ እኩየ ፡ በሑረቱ ፡ ወተከሥተ ፡ አበሳሁ ፡ ወጸንዐ ፡ በዝ ፡ ድልው ፡ ለሊቃውንት ፡ ከመ ፡ ይፍትሑ ፡ ላዕሌሁ ፡ በከመ ፡ ፍትሐ ፡ ቀኖና ፡ ወለሕዝብስ ፡ በሙ ፡ ቃለ ፡ እግዚእነ ፡ በእንተ ፡ ምሳሌሁ ፡ ለዝ ፡ ካህን ፡ "ዲበ ፡ መንበረ ፡ ሙሴ ፡ ነበሩ ፡ ጸሐፍት ፡ ወፈሪሳውያን ፡ ኵሎ ፡ ዘይቤሉክሙ ፡ ዕቀቡ ፡ ወግበሩ ፡ ወበአምሳለ ፡ ምግባሮሙስ ፡ ኢትግበሩ" ።

ወእመሰ ፡ ኢተከሥተ ፡ አበሳሁ ፡ ወኢቆመ ፡ ቀዊመ ፡ ባቲ ፡ ኢይደሉ ፡ አውድቆቱ ፡ ወዘይኴንኖሂ ፡ እመ ፡ ኮነ ፡ ትሩፈ ፡ ገድል ፡ ይትዐቀብ ፡ እምቃሉ ፡ ለእግዚእነ ፡ ዘይቤ ፡ "ኢትኰንኑ ፡ ከመ ፡ ኢትትኰነኑ" ። ወእምቃሉ ፡ ለጳውሎስ ፡ ሐዋርያሁ ፡ ዘይቤ ፡ በአምሳለ ፡ ዝንቱ ፡ "ኩኑ ፡ ዕቁባነ ፡ ከመ ፡ ኢትስሐቱ ፡ አንትሙ ፡ ካዕበ" ። ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ "ምንትኑ ፡ አንተ ፡ አ ፡ ዘትኴንን ፡ ገብረ ፡ ዘኢኮነ ፡ ለከ ፡ እመኒ ፡ ቆመ ፡ አው ፡ ወድቀ ፡ ውእቱ ፡ ለእግዚኡ ፡ ኢትኰንኖ ፡ ለእኁከ ፡ ወኢታስተሐቅሮ ። ወንሕነሰ ፡ ኵልነ ፡ ሀለወነ ፡ ከመ ፡ ንቁም ፡ ቅድመ ፡ መንበሩ ፡ ለክርስቶስ ፡ ወኵሉ ፡ እም

ስለ ፡ ካህናት ፡ ሁሉ ።

፫፻፴፯ ዶቅ ፡ ፵፩ ፡ ፵፪ ፡ ከካህናትና ፡ ከመነኰሳት ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ አገልጋዮች ፡ ወገን ፡ ለአንዱስ ፡ እንኳ ፡ ከቦታው ፡ ወደ ፡ ንግድ ፡ ቦታ ፡ ሊሄድ ፡ አይገባም ። ሌሎችም ፡ መነኰሳት ፡ ኤጲስቆጳሱ ፡ ሳያውቅ ፡ ሳይጸልይ ፡ ሳያዝዝ ፡ የሃይማኖቱንና ፡ የክህነቱን ፡ ሹመት ፡ የሚያስረዳ ፡ ደብዳቤ ፡ ሳይጽፍ ፡ ሊሄድ ፡ አይገባም ።

፫፻፴፰ ረስጠጅ ፡ ፲፪ ፡ ክህነትን ፡ የሰጠው ፡ የኤጲስ ፡ ቆጶሱ ፡ ደብዳቤ ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ባይኖር ፡ በካህናት ፡ ቍጥር ፡ ውስጥ ፡ አግብተው ፡ አይቀበሉት ። የተቀበለውም ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ይለይ ። በውግዘት ፡ የተለየውም ፡ መለየቱ ፡ ይቆያል ።

፫፻፴፱ ፲፩ ፡ ከተወገዘው ፡ ወይም ፡ ከተለየው ፡ ጋር ፡ የተነጋገረ ፡ ወይም ፡ ከነርሱ ፡ ጋር ፡ የጸለየ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይለይ ።

፫፻፵ ክፍል ፡ ስለ ፡ ካህኑ ፡ ይስነካከል ፡ ዘንድ ፡ አንዱስ ፡ እንኳ ፡ አይገባውም ። ከሊቃውም ፡ በቀር ፡ ይቀጣው ፡ ዘንድ ፡ አይገባውም ። መጽሐፍ ፡ ግን ፡ ያስረዳል ። ካህን ፡ ባኗኗሩ ፡ በጎ ፡ ቢሆን ፡ በስምምነት ፡ ሊያከብሩትና ፡ ሊታዘዙለት ፡ እንጂ ፡ ሊቀጡት ፡ አይገባምና ። በአካሄዱ ፡ ክፉ ፡ ቢሆን ፡ በደሉም ፡ ቢታወቅ ፡ በዚህም ፡ ቢፀና ፡ ሕጉ ፡ እንደሚያዝዘው ፡ ፍርድ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ይፈርዱ ፡ ዘንድ ፡ ለሊቃውንት ፡ ይገባል ። ለሕዝቡ ፡ ግን ፡ ስለዚህ ፡ ካህን ፡ ምሳሌ ፡ የጌታችን ፡ ትምህርት ፡ አላቸው ። "በሙሴ ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ጸሐፍት ፡ ፈሪሳውያን ፡ ተቀመጡ ፡ የሚሏችሁን ፡ ሁሉ ፡ ጠብቁ ፡ ሥሩም ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ሥራቸው ፡ ያለውን ፡ ግን ፡ አትሥሩ" ፡ (ማቴ ፡ ፳፫፡ ፪-፫) ። በደሉ ፡ ባይገለጽ ፡ ግን ፡ በርሷም ፡ መጽናትን ፡ ባይጸና ፡ ሊሽሩት ፡ አይገባም ። የሚቀጣውም ፡ የገድል ፡ ትሩፋት ፡ ባለቤት ፡ ቢሆን ፡ "እንዳይፈረድባችሁ ፡ አትፍረዱ" ፡ (ማቴ ፡ ፯-፩ ። ካለው ፡ ከጌታችን ፡ ቃል ፡ የተነሣ ፡ ይጠበቅ ። በዚህም ፡ አምሳል ፡ ካለው ፡ ከሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ ቃል ፡ የተነሣ ፡ "ደግመኛም ፡ እናንተ ፡ እንዳትበድሉ ፡ የተጠበቃችሁ ፡ ሁኑ" ፡ (ገላ ፡ ፯ ፡ ፪) ። ደግመኛም ፡ "የአንተ ፡ የያይደለውን ፡ ባሪያ ፡ የምትነቅፈው ፡ አንተ ፡ ምንድን ፡ ነህ ? አለ ፡ ቢቆም ፡ ወይም ፡ ቢወድቅ ፡ ለጌታው ፡ ነው ። ወንድምህን ፡ አትፍረድበት ፡ አታቃለውም ፡

ኔነ ፡ ለስፉዱ ፡ ያወሥእ ፡ በእንተ ፡ ነፍሱ ።

፫፻፵ ወይእዜኒ ፡ ኢንትኳነን ፡ እምድኅረዝ ፡ በበይናቲነ ፡ እስመ ፡ ንመስሎ ፡ በግብሩ ። "ወንትገሠፅ ፡ ዓዲ ፡ በቃለ ፡ እግዚእነ ፡ ዘይቤ ፡ "በከመ ፡ ኰነንክሙ ፡ ትትኴነኑ ፡ ወበመስፈርት ፡ ዘሰፈርክሙ ፡ ይሰፍሩ ፡ ለክሙ ። ለምንት ፡ ትሬኢ ፡ ሐሠረ ፡ ዘውስተ ፡ ዓይነ ፡ እኁከ ፡ ወኢትሬኢ ፡ ሠርዌ ፡ ዘውስተ ፡ ዓይንከ ፡ አ ፡ መድልው ፡ አውፅእ ፡ ቅድመ ፡ ሠርዌ ፡ እምዓይንከ ፡ ወእምዝ ፡ ትሬኢ ፡ ለአውፅአ ፡ ሐሠረ ፡ እምዓይነ ፡ እኁከ" ወይቤ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ "እልብከ ፡ ምክንያት ፡ አ ፡ ብእሲ ፡ ዘትኴንኖ ፡ ለእኁከ ፡ እስመ ፡ አንተ ፡ በዘትኴንኖ ፡ ለእኁከ ፡ ቦቱ ፡ ትኴንን ፡ ነፍሰከ ፡ ወትግእዛ ። ምንትኑ ፡ ይመስለከ ፡ አ ፡ ብእሲ ፡ ሶበ ፡ ትኴንኖሙ ፡ ለእለ ፡ ይገብርዋ ፡ ለዛቲ ፡ እኪት ፡ እንዘ ፡ አንተ ፡ ትገብራ ፡ ቦኑ ፡ ትክል ፡ ጉይየ ፡ እምነኰነኔሁ ፡ ለእግዚአብሔር ።

፫፻፵፩ ወብየኔ ፡ ልባዊኒ ፡ እስመ ፡ ክህነት ፡ ኀይል ፡ አምላካዊት ፡ ትኄሉ ፡ ውስተ ፡ ልበ ፡ ካህን ፡ ወይበርህ ፡ ባቲ ፡ ልቡናሁ ፡ ወያጸንዖ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባቲ ፡ እመንገለ ፡ ዘይሠይሞ ፡ ለፍጻሜ ፡ በቀኖናተ ፡ ሕዝብ ፡ ዘእርኮን ፡ ሎቱ ፡ ለዘሰፉ ፡ ይእቲ ፡ በቀኖናተ ፡ ሕዝብ ፡ ወሠንዮቶሙ ፡ ላዕለ ፡ እደዊሁ ። ወእምከመሰ ፡ ኮኑ ፡ ፈቃድ ፡ በእንተ ፡ ውሂቦቱ ፡ ክህነተ ፡ ስረዮን ፡ ነፍሱ ፡ ወለሕዝብ ፡ ኅቡረ ፡ ኢይትኀደግ ፡ እንከ ፡ ለእመ ፡ ይገብር ፡ በዘይደሉ ፡ ላቲ ፡ በእንተ ፡ ነፍሱ ፡ ወሕዝቡ ፡ ወአልቦ ፡ ዓመፃ ፡ በእንተ ፡ ፍጻሜሁ ፡ ይደልዎ ፡ ዕሤት ፡ ካዕበተ ፡ ቅድመ ፡ በእንተ ፡ ነፍሱ ፡ ወበእንተ ፡ ሕዝቡ ። ወለእመሰ ፡ ኢፈጸመ ፡ በርቱዕ ፡ ገቢረ ፡ ንስሓ ፡ ወእዕረቀ ፡ ነፍሶ ፡ እምክህነት ፡ ይደልዎ ፡ ኰነኔ ፡ ካዕበተ ፡ በነፍሱ ፡ ወበእንተ ፡ ሕዝቡ ፡ ወዘአልቦ ፡ አበሳ ፡ ላዕሌሁ ፡ በነፍሱ ፡ ይደልዎ ፡ ኰነኔ ፡ በእንተ ፡ ሕዝቡ ፡ ዘከመ ፡ ግብሩ ፡ ለደፋኔ ፡ ወርቀ ፡ እግዚኡ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ተኰ



እኛ ፡ ግን ፡ ሁላችን ፡ በክርስቶስ ፡ ዘፋን ፡ ፊት፡ እንቆም ፡ ዘንድ ፡ አለን ። ከእኛ ፡ ወገን ፡ ሁሉም፡ እያንዳንዱ ፡ ስለ ፡ ስውነቱ ፡ መልስ ፡ ይሰጣል" (ሮሜ ፡ ፲፬ ፡ ፬-፲፩) ።

፫፻፵ ዛሬም ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እርስ ፡ በርሳችን ፡ አንፈራረድ ፡ በሥራው ፡ እንመስለዋለንና ፡ ዳግመኛም ፡ "በፈረዳችሁበት ፡ ይፈረድባችኋል ፡ በሠፈራችሁት ፡ ይሠፍሩላችኋል" ፡ (ማቴ ፡ ፯ ፡ ፪-፯) ። ባስው ፡ በጌታችን ፡ ትምህርት ፡ እንመከር ። "በዓይንህ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ጉድፍ ፡ ሳታይ ፡ በወንድምህ ፡ ዓይን ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ጉድፍ ፡ ለምን ፡ ታያለህ ? አንተ ፡ ግብዝ ፡ አስቀድመህ ፡ የዓይንህን ፡ ጉድፍ ፡ አውጣ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የወንድምህን ፡ ዓይን ፡ ጉድፍ ፡ ለማውጣት ፡ ታያለህ" (ማቴ ፡ ፯ ፡ ፫ - ፯) ። ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ "ሰው ፡ ሆይ ፡ ወን. .ምህን ፡ የምትነቅፍበት ፡ ምክንያት ፡ የለህም ፡ አለ ። አንተ ፡ ወንድምህን ፡ በምትፈርድበት ፡ ገንዘብ ስውነትህን ፡ ትፈርድበታለህና ፡ ታስነቅፋትም አለህ ። ሰው ፡ ሆይ ፡ አንተ ፡ የምትሠራ ን ፡ ይህችን ፡ ክፋት ፡ የሚያደርጉትን ፡ በምትፈርድባቸው ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ይመስልሃል ? ከእግዚአብሔር ፡ ፍርድ ፡ ማምለጥ ፡ ትችላለህን ?" ። (ሮሜ ፡ ፪ ፡ ፩-፬) ።

፫፻፵፩ ልባዊ ፡ ፍርድም ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አምላካዊት ፡ የምትሆን ፡ ሥልጣነ ፡ ክህነት ፡ በካህኑ ፡ ልብ ፡ ውስጥ ፡ ትኖራለችና ፡ ልቡናውም ፡ ይበራበታልና ፡ ለዘለዓለሙ ፡ ያደደለ ፡ ለሕዝቡ ፡ ጥቅም ፡ መሐረሻ ፡ ከሾመው ፡ ወገን ፡ በርሷ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያጸናዋልና ፡ ይህችውም ፡ ሕዝቡን ፡ ለመጥቀም ፡ በእጁም ፡ ለመርዳት ፡ ነው ። ራሱንና ፡ ሕዝቡን ፡ በአንድነት ፡ ለመጥቀም ፡ ክህነትን ፡ መስጠት ፡ የሚያሻ ፡ ከሆነ ፡ እንግዲህ ፡ አልቀረም ። ስለራሱና ፡ ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ በሚገባ፡ ሥራ ፡ ጸንቶ ፡ የሚሠራ ፡ ቢሆን ፡ ስለፍጻሜውም ፡ በደል ፡ ባይኖር ፡ አስቀድሞ ፡ ስለራሱና ፡ ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ እጥፍ ፡ ድርብ ፡ ዋጋ ፡ ይገባዋል ። በሚገባ ፡ የንስሓውን ፡ ቀኖና ፡ ባይፈጽም ፡ ግን ፡ ሰውነቱንም ፡ ከክህነት ፡ ቢለይ ፡ በስውነቱ ፡ ስለሕዝቡም ፡ እጥፍ ፡ ድርብ ፡ ቅጣት ፡ ይገባዋል ። በሰውነቱ ፡ ላይ ፡ በደል ፡ የሌለበት ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ ቅጣት ፡ ይገባዋል ። የጌታውን ፡ ወርቅ ፡ እንደቀበረ ፡ ባሪያ ፡ በሰጡት ፡

ነነ ፡ በእንተ ፡ ዘኢተገበረ ፡ ባቲ ፡ በንዋይ ፡
እንተ ፡ ወሀብዎ ። ወለእመሰ ፡ ኮነ ፡ ዘኢያኅ
ጕላ ፡ ወኢያማስና ፡ እላ ፡ በእንተ ፡ ሕዝቡ ፡
ዘእንበለ ፡ በነፍሱ ፡ ወይደልዎ ፡ ዓስበ ፡ ኮነኔ ፡
በእንተ ፡ ነፍሱ ፡ ባሕቲቱ ፡ ወአልቦ ፡ ዕዳ ፡ ላዕ
ሌሁ ፡ በምክንያተ ፡ ሕዝቡ ፡ ወአልቦ ፡ ዕዳ ፡
ላዕለ ፡ ሕዝቡ ፡ በምክንያተ ፡ ዚአሁ ።
፻፶፱ ወጎርጎርዮስ ፡ ቴዎሎጎስ ፡ በድርሳኑ ፡ ራብዕ ፡
ዘይነግር ፡ በእንተ ፡ ጥምቀት ፡ ናሁ ፡ አስተማ
ስለ ፡ በሰምዕ ፡ ሕዝበ ፡ ሥናየ ፡ ወእኩየ ፡ ወካህና
ተ ፡ እምኔሆሙ ፡ በ፪ቱ ፡ ማኅተም ፡ ፩ዱ ፡ እም
ኔሆሙ ፡ ዘወርቅ ፡ ወካልኡ ፡ ዘሐጺን ፡ ዘተሐንፈጠ ፡
ውስቴቶሙ ፡ አርአያ ፡ ፩ ፡ ንጉሥ ፡ ወሶበ ፡ ተኀትመ ፡
ቦሙ ፡ ስምዕ ፡ አልቦ ፡ ፍልጠት ፡ ውስቴ ፡ ሕፍ
ጠት ፡ ዘአርአያ ፡ ንጉሣዊ ፡ ማእከለ ፡ ዘተኀ
ትመ ፡ በማኅተመ ፡ ወርቅ ፡ ወማእከለ ፡ ዘተኀ
ትመ ፡ በማኅተመ ፡ ሐጺን ፡ ወኢይትሀወቅ ፡
እመ ፡ ደኃረ ፡ እይ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘኀቱም ፡ በወ
ርቅ ፡ እምዘኀቱም ፡ በሐጺን ፡ ወባሕቱ ፡ ፍልጠ
ትሰ ፡ ማእከለ ፡ ዘይትዌከፎ ፡ ለዘየኀትምዎ ፡
ቦቱ ፡ ወማእከለ ፡ ዘኢይትዌከፎ ፡ ወለግልፈ
ትሰ ፡ አልቦ ፡ ፍልጠት ፡ ውስቴ ፡ አርአያሁ ።
ወዓዲ ፡ እስመ ፡ ካህን ፡ ሕጹጸ ፡ ምግባር ፡ ከመ ፡
ማኅቶት ፡ ዘሰምዕ ፡ ወእሳት ፡ ንደታ ፡ ይትሜ
ሰል ፡ በክህነቱ ፡ እሳትኒ ፡ ያውዕያ ፡ ለሰምዕ ፡
ወያበርህ ፡ ለሕዝብ ፡ ወኢይረክቦሙ ፡ ሕሡም ፡
እምውዕየተ ፡ ዚአሃ ።

፻፷ ናምጽእኬ ፡ካልእተ ፡ ምሳሌ ፡ በእንተ ፡ ዛቲ ፡
ፍካሬ ፡ እም፪ቱ ፡ ሰብእ ፡ ፩ዱ ፡ ኄር ፡ ወ፩ዱ ፡ እኩይ
ወቦሙ ፡ ፪ቱ ፡ መፍቅድ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ወዕ
ሩይ ፡ መፍቅዶሙ ፡ ወለንጉሥ ፡ ቦቱ ፡ ፪ቱ ፡
መኳንንት ፡ ፩ዱ ፡ ኄር ፡ ወ፩ዱ ፡ እኩይ ፡ ወአስ
ተብቍዖ ፡ ውእቱ ፡ ኄር ፡ ብእሲ ፡ ለመኰንን ፡
እኩይ ፡ ከመ ፡ ይፈጽም ፡ሎቱ ፡ መፍቅዶ ፡
ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ወብእሲኒ ፡ እኩይ ፡ አስተብቍዖ ፡
ለመኰንን ፡ ኄር ፡ ከማሁ ፡ ለፈጽሞ ፡ መፍቅዶ።
ወንጉሥሰ ፡ ራትዕ ፡ ውእቱ ፡ ወኮነ ፡ የእምር ፡
መፍቅዶሙ ፡ ለ፪ኢሆሙ ፡ መኳንንቲሁ ።
ወሶበ ፡ አስተብቍዕዎ ፡ መኳንንት ፡ ለንጉሥ ፡
በእንተ ፡ መፍቅዶሙ ፡ ሠለጠ ፡ መፍቅዶ ፡
ለኄር ፡ በእደ ፡ መኰንን ፡ እኩይ ፡ ወኢከልአ ፡
መፍቅዶ ፡ በእንተ ፡ እከዩ ፡ ለመኰንን ፡ ዚአሁ ።



ገንዘብ ፡ ስላልሠራበት ፡ እርሱ ፡ ተፈርዶበ
ታልና ፡ ፈጽሞ ፡ ያላጠፋት ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ስለ
ራሱ ፡ ያይደለ ፡ ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡
ስለ ፡ ራሱ ፡ ብቻ ፡ የቅጣት ፡ ዋጋ ፡ ይገባዋል ።
በሕዝቡ ፡ ምክንያት ፡ ዕዳ ፡ የለበትም ፡ በር
ሱም ፡ ምክንያት ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ዕዳ ፡ የለባ
ቸውም ።
፻፶፱ ነባቢ ፡ መለኮት ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ስለ ፡ ጥምቀት ፡
በሚናገረው ፡ በአራተኛው ፡ ድርሳኑ ፡ እነሆ ፡
ክፉውንና ፡ በጎውን ፡ ሰው ፡ በሰምዕ ፡ ከነርሱ ፡
ካህናትን ፡ በሁለት ፡ ማኅተም ፡ መሰሎ ፡ ተና
ገረ ። ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ የወርቅ ፡ ሁለተኛው ፡
የብረት ፡ ሁኖ ፡ በውስጣቸው ፡ የአንድ ፡
ንጉሥ ፡ መልክ ፡ የተቀረጸባቸው ፡ ናቸው ።
ስምዕ ፡ በታተመባቸውም ፡ ጊዜ ፡ የንጉሣዊ
ውን ፡ ቅርጽ ፡ በማስገኘት ፡ በወርቅ ፡ ማኅ
ተም ፡ በታተመው ፡ መካከልና ፡ በብረት ፡ ማኅ
ተም ፡ በታተመው ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡
የለም ። በኋላ ፡ ጊዜ ፡ በብረት ፡ ከታተመው ፡
ተለይቶ ፡ በወርቅ ፡ የታተመው ፡ አይታወ
ቅም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ መለየየትስ ፡ የሚያትሙ
በትን ፡ በሚቀበለውና ፡ በማይቀበለው ፡ መካ
ከል ፡ ነው ። ለሥራ ፡ ግን ፡ በቅርፁ ፡ ልዩነት ፡
የለም ። ዳግመኛ ፡ ምግባር ፡ የጐደለው ፡ ካህን ፡
እንደሰም ፡ መብራት ፡ ነው ። የሚነደው ፡ እሳት
በክህነቱ ፡ ይመስላል ፤ እሳቱም ፡ ሰሙን ፡ ያቀ
ልጠዋል ፡ ለሕዝቡ ፡ ግን ፡ ያበራል ፡ ከብርሃኗ ፡
የተነሣ ፡ ጨለማ ፡ አያገኛቸውም ።
፻፷ ስለዚህች ፡ ትርጓሜ ፡ ከሁለት ፡ ሰዎች ፡ ሌላ ፡
ምሳሌ ፡ እናምጣ ፡ አንዱ ፡ ደግ ፡ አንዱ ፡ ክፉ ፡
ነው ። ሁለቱ ፡ ከንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ ፈቃድ ፡ አላ
ቸው ፡ ፈቃዳቸውም ፡ አንድ ፡ ነው ። ለንጉሡም
ሁለት ፡ መኳንንት ፡ አሉት ፡ አንዱ ፡ ደግ ፡
አንዱ ፡ ክፉ ፡ ነው ። ደጉ ፡ ሰው ፡ ከንጉሡ ፡
ፈቃዱን ፡ ይፈጽምለት ፡ ዘንድ ፡ ክፉውን ፡
ዳኛ ፡ ማለደው ። ክፉውም ፡ ሰው ፡ እንደዚሁ ፡
ፈቃዱን ፡ ይፈጽምለት ፡ ዘንድ ፡ ደጉን ፡ ዳኛ ፡
ማለደው ። ንጉሡ ፡ ግን ፡ እዋቂ ፡ ነው ። የሁለ
ቱንም ፡ መኳንንት ፡ ሥራቸውን ፡ ያውቃል ።
መኳንንቱ ፡ ስለ ፡ ጓዳኞቻቸው ፡ ንጉሡን ፡ በማለ
ዱት ፡ ጊዜ ፡ የደገኛውን ፡ ፈቃድ ፡ በክፉው ፡
ዳኛ ፡ እጅ ፡ ጨረሰ ። የዳኛው ፡ ክፋት ፡ ፈቃ
ዱን ፡ አልከለከለበትም ፡ የክፉውን ፡ ፈቃ

ወኢሠለጠ ፡ መፍቅዶ ፡ ለእኩይ ፡ ላዕለ ፡ እዶ ፡ መኰንን ፡ ኄር ፡ ወኢበቍዖ ፡ ኂርውናሁ ፡ ለመኰንን ፡ በእንተ ፡ እከየ ፡ ዚአሁ ፡ ወለእመኒ ፡ ረብኀ ፡ ወተጸገወ ፡ እግዚአብሔር ፡ የአምር ።

ድ ፡ በደጉ ፡ ዳኛ ፡ እጅ ፡ አልጨረሰም ፡ ስለርሱ ፡ ክፋት ፡ የዳኛው ፡ ደግነት ፡ አልጠቀመውም ፡ ቢቀበልና ፡ ቢጠቀምም ፡ እንጃ ! እግዚአብሔር ፡ ያውቃል ።

## አንቀጽ ፡ ፲ ።

በእንተ ፡ መንኰሳት ፡ ወመንኰሳይያት ።

፻፷፩ ወውእቱ ፡ ጟቱ ፡ እክፉል ፡ ቀዳማዊ ፡ በእንተ ፡ ነገሮሙ ፡ ምንኩስናስ ፡ ጥበበ ፡ ሕግ ፡ መሚሐዊት ፡ ይእቲ ፡ ወመንኰሳትኒ ፡ መላእክት ፡ ምድራውያን ፡ ወሰብእ ፡ ሰማያውያን ፡ እሙንቱ ፡ ተላውያኒሁ ፡ ለክርስቶስ ። በከመ ፡ ክሂሎቶሙ ። ወበኵሉ ፡ ምግባራቲሆሙ ፡ ተመሳልያን ፡ በሐዋርያቲሁ ፡ በተግኅሦ ፡ እምጥሪታተ ፡ ዓለም ፡ ውኅዲገ ፡ ፍትወታቲሁ ፡ ወመንኖ ፡ ኵሉ ፡ ግብር እስከ ፡ ነፍሳቲሆሙ ፡ በእንተ ፡ ተአዝዞቱ ፡ ወአፍቅሮቱ ፡ ወገቢርያን ፡ ትእዛዙ ፡ እንተ ፡ አዘዞሙ ፡ ባቲ ፡ ለፈቃድያን፡ ፍጻሜ ፡ መፍቀርያኒሁ ፡ ሎቱ ፡ ለባሕቲቱ ፡ ፈድፋደ ፡ እምአበው ፡ ወውሉድ ፡ ወብእሲት ፡ ወንዋይ ። ወእሙንቱ ፡ ብፁዓን ፡ በእንተ ፡ ዕረፍት ፡ እምድካም ፡ ዘይእዜ ፡ ዘይገብርዋ ፡ በፈቃዶሙ ፡ ወበእንተ ፡ ድኂን ፡ ወተባልሖ ፡ እምነኒኔ ፡ ደኃሪት ፡ ዘለዓለም ። ወብፁዓንሰ ፡ እሙንቱ ፡ ፈድፋደ ፡ ብፁዓን ፡ በእንተ ፡ ዘተደለወ ፡ ሎሙ ፡ ማኅደረ ፡ መንግሥት ፡ ሰማያዊ ፡ በእንተ ፡ ድካም ፡ ኀላፊ ፡ ዘይገብርዎ ፡ በሥምረቶሙ ።

፻፷፪ ዳግም ፡ ክፍል ፡ በእንተ ፡ ትእዛዝ ፡ ዘይደሉ ፡ ያቤ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ "ትፈቅድኑ ፡ ከመ ፡ ትኩን ፡ ፍጹመ ፡ ሑር ፡ ወሢጥ ፡ ኵሎ ፡ ዘብከ ፡ ወሀብ ፡ ለነዳያን ፡ ወነዓ ፡ ትልወኒ" ። ወዘንተ ፡ ይቤሎ ፡ ለዘይቤሎ ፡ "ምንተ፡ እግበር ፡ ከመ ፡ እረስ ፡ ሕይወተ ፡ ዘለዓለም" ፡ ወሶበ ፡ ነገሮ ፡ ትእዛዛተ ፡ ይቤ "ዘንተሰ ፡ ዐቀብኩ ፡ እምንእስየ ፡ ምንትኑ ፡ ዘተርፈኒ" ። ወይቤሎሙ ፡ ለአርዳኢሁ ፡ ዘያፈቅር ፡ አበ ፡ ወእመ ፡ ፈድፋደ ፡ እምኔየ ፡ ኢይደሉ ፡ ሊተ ፡ ወዘያፈቅር ፡ ወልዶ ፡ ወወለቶ ፡ ፈድፋደ ፡ እምኔየ ፡ ኢይደሉ ፡ ሊተ ፡ ወዘኢያረ ፡ መስቀለ ፡ ሞቱ ፡ ወኢተለወኒ ፡ ኢይደሉ ፡ ሊተ ።

## አንቀጽ ፡ ዓሥር ።

ስለ ፡ ወንዶች ፡ መንኰሳትና ፡ ስለ ፡ ሴቶች ፡ መንኰሳት ፡ ይናገራል ።

፻፷፩ ይኸውም ፡ ስምንት ፡ ክፍል ፡ ነው ፡ መጀመሪያ፡ ስለሁኔታቸው ፡ ይናገራል ። ምንኩስናስ ፡ የመሚሐዊት ፡ ሕግ ፡ ጥበብ ፡ ናት ። መንኰሳትም ፡ ምድራውያን ፡ መላእክት ፡ ሰማያውያን ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ። እንደችሎታቸው ፡ መጠን ፡ የክርስቶስ ፡ ተከታዮች ፡ በሥራቸውም ፡ ሁሉ ፡ የሐዋርያት ፡ ምሳሌዎች ፡ ናቸው ። ከዓለም ፡ ጥሪት ፡ በመለየት ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋን ፡ በመተው ፡ እስከ ፡ ሰውነታቸው ፡ ድረስ ፡ ሥራውን፡ ሁሉ ፡ በመናቅ ፡ ስለ ፡ ትእዛዙ ፡ ስለ ፡ ፍቅሩ ፡ ፈቃዱን ፡ ለመፈጸም ፡ ያዘዛቸውን ፡ ትእዛዝ ፡ ስለሚያደርጉ ፡ እርሱንም ፡ ብቻ ፡ ከአባቶች ፡ ከልጆች ፡ ከሚስት ፡ ከገንዘብ ፡ ይልቅ ፡ ፈጽሞ ፡ ስለሚወዱ ፡ ነው ። ዛሬ ፡ በፈቃዳቸው ፡ ከሚሠሩት ፡ ድካም ፡ ዕረፍት ፡ ስለማድረግ ፡ ከኋለኛውም ፡ ዓለም ፡ ፍርድ ፡ ፈጽሞ ፡ ስለመዳን ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ። ብፁዓን ፡ ግን ፡ በፈቃዳቸው ፡ ስለሚሠሩት ፡ ስለ ፡ ኀላፊው ፡ ድካም ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ማደሪያ ፡ ስለተዘጋጀላቸው ፡ ፈጽሞ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ።

፻፷፪ ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ስለሚገባው ፡ ትእዛዝ ፡ ይናገራል ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንዲህ፡ አለ ። "ፍጹም ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ትወዳለህን ?" ያለህን ፡ ሁሉ ፡ ሂደህ ፡ ሽጠህ ፡ ለነዳያንም ፡ መጽውተህ ፡ ና ፡ ተከተለኝ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወትን ፡ እወርስ ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ላድርግ ፡ ላለው ፡ ይህን ፡ መለሰለት ።" ትእዛዙን ፡ በነገረው ፡ ጊዜ ፡ «ይህንስ ፡ ከትንሽነቴ ፡ ጀምሬ ፡ ጠብቄዋለሁ ፡ የቀረኝ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ አለ ። (ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፳፩-፳፪) ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ ከኔ ፡ ይልቅ ፡ እባቱንና ፡ እናቱን ፡ የወደደ ፡ ለእኔ ፡ ሊሆን ፡ አይገባም ፡ አላቸው ፡ ከኔም ፡ ይልቅ ፡ ወንድ ፡ ልጁንና ፡ ሴት ፡ ልጁን ፡ የሚወድ ፡ ለእኔ ፡ ሊሆን ፡ አይገባም ፡ የሞቱን ፡ መስቀል ፡

ወኢሠለጠ ፡ መፍቅዶ ፡ ለእኩይ ፡ ላዕለ ፡ እደ ፡ መኰንን ፡ ኄር ፡ ወኢበቍዖ ፡ ኂሮውናሁ ፡ ለመኰንን ፡ በእንተ ፡ እከየ ፡ ዚአሁ ፡ ወለእመኒ ፡ ረብሐ ፡ ወተጸገወ ፡ እግዚአብሔር ፡ የአምር ።

## አንቀጽ ፡ ፲ ።

በእንተ ፡ መንኰሳት ፡ ወመንኰሳይያት ።

፲፻፶፬ ወውእቱ ፡ ቋቱ ፡ እክፍል ፡ ቀዳማዊ ፡ በእንተ ፡ ነገሮሙ ፡ ምንኵስናስ ፡ ጥበበ ፡ ሕግ ፡ መሚሐዊት ፡ ይእቲ ፡ ወመንኰሳትኒ ፡ መላእክት ፡ ምድራውያን ፡ ወሰብእ ፡ ሰማያውያን ፡ እሙንቱ ፡ ተላውያኒሁ ፡ ለክርስቶስ ። በከመ ፡ ክሂሎቶሙ ። ወበኵሉ ፡ ምግባራቲሆሙ ፡ ተመሳልያን ፡ በሐዋርያቲሁ ፡ በተግኅሥ ፡ እምጥሪታተ ፡ ዓለም ፡ ውኂዲን ፡ ፍትወታቲሁ ፡ ወመንኖ ፡ ኵሉ ፡ ግብር እስከ ፡ ነፍሳቲሆሙ ፡ በእንተ ፡ ተአዝዞቱ ፡ ወእፍቅሮቱ ፡ ወገባርያን ፡ ትእዛዙ ፡ እንተ ፡ አዘዞሙ ፡ ባቲ ፡ ለፈቃድያን፡ ፍጻሜ ፡ መፍቀርያኒሁ ፡ ሎቱ ፡ ለባሕቲቱ ፡ ፈድፋደ ፡ እምአበው ፡ ወውሉድ ፡ ወብእሲት ፡ ወንዋይ ። ወእሙንቱ ፡ ብፁዓን ፡ በእንተ ፡ ዕረፍት ፡ እምድካም ፡ ዘይእዜ ፡ ዘይገብርዋ ፡ በፈቃዶሙ ፡ ወበእንተ ፡ ድኂን ፡ ወተባልሖ ፡ እምኵነኔ ፡ ደኃሪት ፡ ዘለዓለም ። ወብፁዓንሰ ፡ እሙንቱ ፡ ፈድፋደ ፡ ብፁዓን ፡ በእንተ ፡ ዘተደለወ ፡ ሎሙ ፡ ማኅደረ ፡ መንግሥት ፡ ሰማያዊ ፡ በእንተ ፡ ድካም ፡ ኀላፊ ፡ ዘይገብርዎ ፡ በሥምረቶሙ ።

፲፻፶፭ ዳግም ፡ ክፍል ፡ በእንተ ፡ ትእዛዝ ፡ ዘይደሉ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ "ትፈቅድኑ ፡ ከመ ፡ ትኩን ፡ ፍጹመ ፡ ሑር ፡ ወሢጥ ፡ ኵሎ ፡ ዘብከ ፡ ወሀብ ፡ ለነዳያን ፡ ወነዓ ፡ ትልወኒ" ። ወዘንተ ፡ ይቤሎ ፡ ለዘይቤሎ ፡ "ምንተ፡ እግበር ፡ ከመ ፡ እረስ ፡ ሕይወተ ፡ ዘለዓለም" ፡ ወሶበ ፡ ነገሮ ፡ ትእዛዛተ ፡ ይቤ "ዘንተሰ ፡ ዐቀብኩ ፡ እምንእስየ ፡ ምንትኑ ፡ ዘተርፈኒ" ። ወይቤሎሙ ፡ ለአርዳኢሁ ፡ ዘያፈቅር ፡ አበ ፡ ወእመ ፡ ፈድፋደ ፡ እምኔየ ፡ ኢይደሉ ፡ ሊተ ፡ ወዘያፈቅር ፡ ወልዶ ፡ ወወለቶ ፡ ፈድፋደ ፡ እምኔየ ፡ ኢይደሉ ፡ ሊተ ፡ ወዘኢያፀረ ፡ መስቀለ ፡ ሞቱ ፡ ወኢተለወኒ ፡ ኢይደሉ ፡ ሊተ ።



ድ ፡ በደጉ ፡ ዳኛ ፡ እጅ ፡ አልሠለጠነም ፡ ስለርሱ ፡ ክፋት ፡ የዳኛው ፡ ደግነት ፡ አልጠቀመውም ፡ ቢቀበልና ፡ ቢጠቀምም ፡ እንጃ ! እግዚአብሔር ፡ ያውቃል ።

## አንቀጽ ፡ ዓሥር ።

ስለ ፡ ወንዶች ፡ መንኰሳትና ፡ ስለ ፡ ሴቶች ፡ መነኰሳት ፡ ይናገራል ።

፲፻፶፬ ይኸውም ፡ ስምንት ፡ ክፍል ፡ ነው ፡ መጀመሪያ፡ ስለሁኔታቸው ፡ ይናገራል ። ምንኵስናስ ፡ የመሚሐዊት ፡ ሕግ ፡ ጥበብ ፡ ናት ። መንኰሳትም ፡ ምድራውያን ፡ መላእክት ፡ ሰማያውያን ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ። እንደችሎታቸው ፡ መጠን ፡ የክርስቶስ ፡ ተከታዮች ፡ በሥራቸውም ፡ ሁሉ ፡ የሐዋርያት ፡ ምሳሌዎች ፡ ናቸው ። ከዓለም ፡ ጥሪት ፡ በመለየት ፡ ፈቃደ ፡ ሥጋን ፡ በመተው ፡ እስከ ፡ ሰውነታቸው ፡ ድረስ ፡ ሥራውን፡ ሁሉ ፡ በመናቅ ፡ ስለ ፡ ትእዛዙ ፡ ስለ ፡ ፍቅሩ ፡ ፈቃዱን ፡ ለመፈጸም ፡ ያዘዛቸውን ፡ ትእዛዝ ፡ ስለሚያደርጉ ፡ እርሱንም ፡ ብቻ ፡ ከአባቶች ፡ ከልጆች ፡ ከሚስት ፡ ከገንዘብ ፡ ይልቅ ፡ ፈጽሞ ፡ ስለሚወዱ ፡ ነው ። ዛሬ ፡ በፈቃዳቸው ፡ ከሚሠሩት ፡ ድካም ፡ ዕረፍት ፡ ስለማድረግ ፡ ከኋለኛውም ፡ ዓለም ፡ ፍርድ ፡ ፈጽሞ ፡ ስለመዳን ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ። ብፁዓን ፡ ግን ፡ በፈቃዳቸው ፡ ስለሚሠሩት ፡ ስለ ፡ ኀላፊው ፡ ድካም ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ማደሪያ ፡ ስለተዘጋጀላቸው ፡ ፈጽሞ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ።

፲፻፶፭ ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ስለሚገባው ፡ ትእዛዝ ፡ ይናገራል ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንዲህ፡ አለ ። "ፍጹም ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ትወዳለህን ?" ያለህን ፡ ሁሉ ፡ ሂደህ ፡ ሽጠህ ፡ ለነዳያንም ፡ መጽውተህ ፡ ና ፡ ተከተለኝ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወትን ፡ እወርስ ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ላድርግ ፡ ላለው ፡ ይህን ፡ መለሰለት ።" ትእዛዙን ፡ በነገረው ፡ ጊዜ ፡ «ይህንስ ፡ ከትንሽነቴ ፡ ጀምሬ ፡ ጠብቄዋለሁ ፡ የቀረኝ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ አለ ። (ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፳፩-፳፪) ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ ከኔ ይልቅ ፡ አባቱንና ፡ እናቱን ፡ የወደደ ፡ ለእኔ ፡ ሊሆን ፡ አይገባም ፡ አላቸው ፡ ከኔም ፡ ይልቅ ፡ ወንድ ፡ ልጁንና ፡ ሴት ፡ ልጁን ፡ የሚወድ ፡ ለእኔ ፡ ሊሆን ፡ አይገባም ፡ የሞቱን ፡ መስቀል ፡

፫፻፵፮ ወይቤ ፡ ባስልዮስ ፡ በመጽሐፈ ፡ ጽሙና ፡ ወመንኖ ፡ ዐለም ፡ "ይደልዎ ፡ መቅድመ ፡ ኵሉ ፡ ግብር ፡ ለዘይመጽእ ፡ ኀበ ፡ ዛቲ ፡ ትሩፋት ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ሎቱ ፡ ሕሊና ፡ ጽኑዕ ፡ ዘኢያንቀለቅል ፡ ለፈጽሞ ፡ ኪዳን ፡ ዘተካየዶ ፡ ወኢይግባእ ፡ ኀበ ፡ ድኅር ፡ ወከመ ፡ ይፈጽም ፡ ትእዛዘሙ ፡ ለሊቃውንት ፡ ዘላዕሌሁ ፡ ወይኅሥሥ ፡ ዘይደሉ ፡ ለመድኃኒተ ፡ ነፍሱ" ።

፫፻፵፯ ዘኒቅያ ፡ እሐዱ ፡ ወኢይባእ ፡ ኀበ ፡ ምንኵስና ፡ ዘቦቱ ፡ መንፈስ ፡ ጋኔን ።

፫፻፵፰ ዘ፲ወ፰ቱ ፡ ወለእመ ፡ ኀሠሠ ፡ እሐዱሂ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ መነኮሰ ፡ ዘእንበለ ፡ መባሕተ ፡ ኤጲስ ቆጶስ ፡ ዘውእቱ ፡ ሀሎ ፡ ታሕተ ፡ ሥልጣኑ ፡ ኢይትወከፍዎ ፡ ለምንኵስና ፡ ከመ ፡ ኢይኩን ፡ ሎቱ ፡ ምክንያት ፡ በእንተ ፡ ብእሲት ፡ ወውሉድ ፡ ወእም ፡ ወዘይመስሎ ፡ ለዝንቱ ።

፫፻፵፱ ግንር ፡ ፲ወ፰ቱ ፡ ፲ወ፱ቱ ፡ ዘየኀድግ ፡ ውሉዶ ፡ ወኢይሴሰዮሙ ፡ ወኢየሐፅኖሙ ፡ በምክንያተ ፡ መልእክተ ፡ እግዚአብሔር ፡ እው ፡ ኀደገ ፡ እበዊሁ ፡ ወፈድፋደሰ ፡ እንዘ ፡ ውእቶሙ ፡ ምእመናን ፡ ወዘኢያከብሮሙ ፡ በምክያተ ፡ ተፀምዶ ፡ ይኩን ፡ ውጉዘ ።

፫፻፶ ዘኒቅያ ፡ ምንኵስናሰ ፡ እምፈቃድ ፡ ይእቲ ፡ ወእኮ ፡ በግብር ። ወቦ ፡ በጽሐ ፡ ፩ዱሂ ፡ ኀበ ፡ ምኔት ፡ ከመ ፡ ይመንኵስ ፡ ወይንበር ፡ ውስቴቱ ፡ ይሕትቶ ፡ ርእሰ ፡ ደብር ፡ ሐተታ ፡ ፅኑዐ ፡ እምአይቴ ፡ ውእቱ ፡ ወምንት ፡ ግብሩ ፡ ወበምንት ፡ ምክንያት ፡ ተማኅፀነ ፡ ኀበ ፡ ምኔቶሙ ። ወለእመ ፡ ሎቱ ፡ ብእሲት ፡ ወውሉድ ፡ ወፈቀደ ፡ ይጕየይ ፡ እምኔሆሙ ፡ በእንተ ፡ ክበደ ፡ ዘመን ።

፫፻፶፩ ወለእመኒ ፡ ኮነ ፡ ገብረ ፡ ለአሐዱ ፡ እምእመናን ፡ ኢይትወከፍዎ ፡ ዘእንበለ ፡ መባሕተ ፡ እግዚኡ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ግዑዘ ፡ እምውሉደ ፡ ምእመናን ፡ ወውእቱ ፡ ወሬዛ ፡ ዘሀሎ ፡ ውስተ ፡ ምግበ ፡ አቡሁ ፡ ወኢፈቀደ ፡ ምንኵስናሁ ፡ ኢይትወከፍዎ ። እመሰ ፡ ኮነ ፡ በባሕቲቱ ፡ ወተፈልጠ ፡ እምኔሆሙ ፡ እምብዙኅ ፡ አዝማን ፡ ወቀነየ ፡ ነፍሶ ፡ ይትወከፍዎ ።

፫፻፶፪ ወለእመ ፡ ኮነት ፡ ሎቱ ፡ ብእሲት ፡ ወኢፈቀደት ፡ ምንኵስናሁ ፡ ኢይትወከፍዎ ። ወለእ



ተሸክሞ ፡ ያልተከተለኝ ፡ ለእኔ ፡ ሊሆን ፡ አይገባም ። » (ማቴ ፡ ፲ ፡ ፴፯ - ፴፰) ።

፫፻፵፮ ባስልዮስ ፡ በምንኵስናና ፡ ዓለምን ፡ በናቀበት ፡ መጽሐፉ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ወደዚህች ፡ ትሩፋት ፡ የሚመጣ ፡ ሰው ፡ ከሥራው ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ የማለውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ለመፈጸም ፡ የማይነዋወጥ ፡ ጽኑ ፡ ሕሊና ፡ ሊኖረው ፡ ይገባል ፡ ወደኋላ ፡ አይመለስ ፡ በበላዩ ፡ ያሉ ፡ የሊቃውንቱን ፡ ትእዛዝ ፡ ይፈጽም ፡ ዘንድ ፡ ሰውነቱን ፡ ለማዳን ፡ የሚገባውን ፡ ይሻ ።

፫፻፵፯ ኒቅያ ፡ ፩ ፡ መንፈስ ፡ ጋኔን ፡ ያደረበት ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ምንኵስና ፡ አይግባ ።

፫፻፵፰ ፲፰ ፡ ከሥልጣኑ ፡ በታች ፡ ያለ ፡ አንዱስ ፡ እንኳ ፡ ያለ ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ ፈቃድ ፡ ሊመነኵስ ፡ ቢፈልግ ፡ ለማመንኰስ ፡ አይቀበሉት ። ስለ ፡ ሚስት ስለ ፡ ልጅ ፡ ስለ ፡ እናት ፡ ይህን ፡ ስለሚመስለውም ፡ የቅሬታ ፡ ምክንያት ፡ እንዳይኖረው ።

፫፻፵፱ ግንር ፡ ፲፰ ፡ ፲፱ ፡ ልጁን ፡ ትቶ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በማገልገል ፡ ምክንያት ፡ የማይመግባቸው ፡ የማይረዳቸውም ፡ ወይም ፡ አባቶቹን ፡ የተወ ፡ ይልቁንም ፡ እነርሱ ፡ ምእመናን ፡ ሲሆኑ ፡ በምንኵስና ፡ ምክንያት ፡ የማይረዳቸው ፡ የተለየ ፡ ይሁን ።

፫፻፶ ኒቅያ ፡ ምንኵስናስ ፡ በግድ ፡ ያይደለ ፡ በፈቃድ ፡ ናት ። አንዱስ ፡ እንኳ ፡ መንኵሶ ፡ በውስጡ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ገዳም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ከየት ፡ እንደሆነ ፡ ሥራውም ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ወደ ፡ ገዳማቸውም ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ እንደ ፡ ተማፀነ ፡ ልጅ ፡ ሚስት ፡ እንዳሉት ፡ ስለ ፡ ዘመኑም ፡ ችግር ፡ ከእነርሱ ፡ ሊያመልጥ ፡ ፈልጎ ፡ እንደሆነ ፡ የገዳሙ ፡ መምህር ፡ በጽኑ ፡ ምርመራ ፡ ይመርምረው ።

፫፻፶፩ ከምእመናን ፡ ወገን ፡ ለአንዱ ፡ አገልጋይ ፡ ቢሆንም ፡ ያለጌታው ፡ ፈቃድ ፡ አይቀበሉት ። ከምእመናን ፡ ልጆች ፡ ነፃ ፡ የወጣ ፡ ቢሆን ፡ ይኸውም ፡ ከአባቱ ፡ አስተዳደር ፡ በታች ፡ ያለ ፡ ጐልማሳ ፡ ነው ። ምንኵስናውን ፡ ባይወድ ፡ አይቀበሉት ። ብቻውን ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ከነርሱ ፡ ቢለይ ፡ ራሱንም ፡ የቻለ ፡ ቢሆን ፡ ይቀበሉት ።

፫፻፶፪ ሚስት ፡ ያለችው ፡ ቢሆን ፡ ምንኵስናውንም ፡ ባትወድ ፡ አይቀበሉት ። ከሚስቱ ፡ የተነሣ ፡

መሳ ፡ ኮነት ፡ ቦቱ ፡ እከይ ፡ ወሕማም ፡ እምብእሲቱ ፡ ወፈቀደ ፡ ተባልሖ ፡ ወኀየ ፡ እምኔሃ ፡ ይትወከፍዎ ።

፻፶፫ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘቀተለ ፡ ሰብእ ፡ ዘኢኮነ ፡ ማእከሌሁ ፡ ጽልእ ፡ ወኢባእስ ፡ እምቀዲሙ ፡ እላ ፡ ኮነ ፡ ቀቲሎቱ ፡ በእዴሁ ፡ ዘእንበለ ፡ ፈቃዱ ፡ ወኀረየ ፡ ምንኵስና ፡ ለንስሓ ፡ ይትወከፍዎ ። ወለእመ ፡ መጽኡ ፡ ሰብእ ፡ ዚእሁ ፡ ለዘተቀትለ እምድኅረ ፡ ምንኵስናሁ ፡ ወፈቀዱ ፡ ይንሥእዎ ፡ ይትጋደል ፡ ርእሰ ፡ ምኔት ፡ ወሰብኡ ፡ ኵሎሙ ፡ ለእድኅኖቱ ። እስመ ፡ ውእቱ ፡ ኢቀተለ ፡ በፈቃዱ ፡ ወኢበቀጺበ ፡ ሰብእ ፡ እላ ፡ ኮነ ፡ ግብር ፡ ዘእንበለ ፡ ፈቃዱ ። እስመ ፡ ውእቱ ተማኅፀነ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ በንስሓ ፡ ወተፀምዶ ፡ ለምንኵስና ፡ በተዓቅቦ ፡ በእንተ ፡ መድኃኒተ ፡ ነፍሱ ፡ ወዝንቱ ፡ እንቀጽ ፡ ዘእንበለ ፡ ግዘት ።

፻፶፬ ሣልስ ፡ በእንተ ፡ ዘይደሉ ፡ ሎቱ ፡ ይግበር ፡ በንዋዩ ፡ በከመ ፡ ይደሉ ፡ ለምንኵስና ። ጠስ ፡ ፷ወ፬ቱ ፡ ወኵሉ ፡ ዘፈቀደ ፡ ምንኵስና ፡ ለእመ ፡ ኢኮነ ፡ ሎቱ ፡ ውሉድ ፡ የእዝዝ ፡ እምቅድመ ፡ ምንኵስናሁ ፡ በእንተ ፡ ንዋዩ ፡ በከመ ፡ ፈቀደ ፡ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ንዋዩ ፡ እምድኅረ ፡ ምንኵስናሁ፡ ይከውን ፡ ለምኔት ።

፻፶፭ በስ ፡ ወናሁ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ "ሑር ፡ ወሢጥ ፡ ኵሎ ፡ ንዋየከ ፡ ወሀቦሙ ፡ ለምስኪናን ፡ ወትዘግብ ፡ ለከ ፡ መዝገበ ፡ በሰማያት ፡ ወነዓ ፡ ትልወኒ" ፡ ወእነ ፡ እብል ፡ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ዘይወፅእ ፡ እምሰብኡ ፡ ወይበውእ ፡ ውስተ ፡ ተቀንዮ ፡ ለእምላክ ፡ ይደሉ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ኢይግድፉ ፡ ንዋዮ ፡ በከንቱ ። እስመ ፡ ይእቲ ፡ ኮነት ፡ ሕርምተ ፡ ለእግዚእብሔር ፡ ዳእሙ ፡ ይሥርዓ ፡ ዘከመ ፡ ፈቀደ ፡ እግዚእብሔር ፡ በፈሊጥ ፡ ወግእዛን ፡ እመኒ ፡ በእዴሁ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ማእምረ ፡ ወምኩረ ። ወእመ ፡ እኮ ፡ ሳዕለ ፡ እደ ፡ ሕዝብ ፡ ኅሩያን ፡ ዘነዋ ፡ እስተርእየ ፡ ሥነ ፡ ምግባሮሙ ፡ ከመ ፡ እሙንቱ ፡ ሠራዕያን ፡ ወማእምራን ፡ ወጠቢባን ፡ ወዕዉቃን ፡ በመግቦቶሙ ፡ እእሚሮ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ሐዋሬ ፡ ፍኖት ፡ ወከመ ፡ የኀድጋ ፡ ለእዝማዲሁ ፡ ሥጋውያን ፡ ለእመ ፡ ኢኮኑ ፡ ጽኑሳነ ። ወእመ ፡ እመገቦ ፡ ለዘኢኮነ ፡ ውእቱ ፡ በከመ ፡ ነገርነ ፡ ወተሠይመ ፡ ለመግ

ሕመምና ፡ ከፋት ፡ ቢሆንበት ፡ ግን ፡ ሊድን ፡ ወድዶ ፡ ከርሷ ፡ ቢለይ ፡ ይቀበሉት ።

፻፶፫ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ጠብ ፡ ክርክር ፡ በመካከሉ ፡ የሌለበትን ፡ ሰው ፡ የገደለ ፡ ቢሆን ፡ አገዳደሉ ፡ ያለ ፡ ፈቃዱ ፡ በእጁ ፡ ሆነ ፡ እንጂ ፡ ለንስሓ ፡ ምንኵስናን ፡ ቢወድ ፡ ይቀበሉት ። ከመነኰሰ ፡ በኋላ ፡ የሟቹ ፡ ሰዎች ፡ ቢመጡ ፡ ሊወስዱትም ፡ ቢወዱ ፡ የገዳሙ ፡ አስተዳዳሪና ፡ ማኅበሩም ፡ ሁሉ ፡ እርሱን ፡ ለማዳን ፡ ይበርቱ ። እርሱ ፡ በፈቃዱ ፡ ወይም ፡ ሰው ፡ ጠቅሶት ፡ አልገደለ ምና ። ያለ ፡ ፈቃዱ ፡ በግድ ፡ ሆነ ፡ እንጂ ፡ እርሱ የሰውነቱን ፡ ደኅንነት ፡ ለመጠበቅ ፡ በንስሓና ፡ ለምንኵስና ፡ ፅሙድ ፡ በመሆን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተማፅኗልና ፡ ይህ ፡ ያልተወገዘበት ፡ እንቀጽ ፡ ነው ።

፻፶፬ ሦስተኛ ፡ ለምንኵስና ፡ እንደሚገባ ፡ በገንዘቡ ፡ ሊያደርገው ፡ ስለሚገባው ፡ ይናገራል ። ጠስ ፡ ፷፬ ፡ ምንኵስናን ፡ የወደደ ፡ ሁሉ ፡ ልጆች ፡ የሌሉት ፡ ቢሆን ፡ ከመመንኰሱ ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡ በገንዘቡ ፡ ይዘዝ ፡ ከመነኰሰ ፡ በኋላ ፡ ገንዘቡ ፡ ሁሉ ፡ ለገዳሙ ፡ ይሆናልና ።

፻፶፭ በስ ፡ እነሆ ፡ ጌታችንና ፡ መድኃኒታችን ፡ «ሂደህ ፡ ገንዘብህን ፡ ሁሉ ፡ ሽጠህ ፡ ለነዳያን ፡ መጽውተህ ፡ በሰማይም ፡ ድልብን ፡ ታከማቻለህ ፡ ና ፡ ተከተለኝ ፡ አለ ።» (ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፳፩)። እኔም ፡ ከወገኑ ፡ ተለይቶ ፡ ለአምላክ ፡ ወደ ፡ መገዛት ፡ የሚገባ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በከንቱ ፡ ገንዘቡን ፡ ማጥፋት ፡ አይገባውም ፡ እኮ ፡ እላለሁ ። ይህች ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተለየች ፡ ሁናለችና ፡ ለእውቀትና ፡ በነፃነት ፡ በእጁም ፡ ቢሆን ፡ አዋቂ ፡ የተፈተነ ፡ ቢሆን ፡ ይህም ፡ ባይሆን ፡ አዛዦች ፡ አዋቂዎች ፡ ብልሀተኞች ፡ በአስተዳደራቸው ፡ የታወቁ ፡ እንደሆኑ ፡ የሥራቸው ፡ ማማር ፡ በተገለጠላቸው ፡ በተመረጡት ፡ ሕዝብ ፡ እጅ ፡ ላይ ፡ ቢሆን ፡ የተቸገሩ ፡ ካልሆኑ ፡ በቀር ፡ መንገደኛ ፡ እንደሆነና ፡ ለሥጋ ፡ ዘመዶቹም ፡ እንደሚተዋት ፡ አውቆ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ይሥራባት ፡ እንጂ ። እንደተናገርነው ፡ ያልሆነውን ፡ ቢሾም ፡ ለአስተዳደሯም ፡ ቢሾም ፡ «እነሆ ፡ በስንፍና ፡ የእግ

ቦታ ፡ ወነዋ ፡ ጽሑፍ ፡ ዘይቤ ፡ ርትዕ ፡ ውእቱ ፡ ኵሉ ፡ ዘይገብር ፡ ግብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሀኬት ፡ ወለንትዐቀብ ፡ እምኵሉ ፡ ገጽ ፡ ከመ ፡ እመንገለ ፡ ሀኬትነ ፡ ኢንትረከብ ፡ ተዓዳውያነ ፡ ለትእዛዙ ፡ በምክንያተ ፡ ፈጽሞተ ፡ ትእዛዝ ፡ ካልእ ። በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ይደልወነ ፡ ካዕበ ፡ ከመ ፡ ኢንጽልአሙ ፡ ለእለ ፡ ይነሥኡነ ፡ በጽልእ ፡ ወቀትል ፡ በእንተ ፡ ምንትኒ ፡ እምንዋይነ ።

፲፻፺፮ ራብዕ ፡ በዘይትእኀዙ ፡ ወይእቲ ፡ በዝንቱ ፡ እንቀጽ ፡ ስሱ ፡ እማንቱ ፡ ቀዳሚት ፡ እምኔሆን ፡ ኀዲገ ፡ አውስቦ ፡ ወእምኔሆሙ ፡ ዘኢያውሰበ ፡ ግሙራ ፡ ወእምኔሆሙ ፡ ዘአውሰበ ፡ ወእምዝ ፡ ተፈልጠ ፡ እምብእሲቱ ። ወቀዳማውያንሰ ፡ ውእቶሙ ፡ ዘይቤ ፡ እግዚእነ ፡ በእንቲአሆሙ ፡ "ወቦ ፡ ሕጽዋን ፡ ዘሐጸዉ ፡ ርእሶሙ ፡ በእንተ ፡ መንግሥተ ፡ እግዚአብሔር ። ወካልእንሂ ፡ ተለዉ ፡ ቃሎ ፡ ዘይቤ ፡ "ዘኀደገ ፡ ብእሲቶ ፡ በእንቲአየ ፡ ሎቱ ፡ ሕይወት ፡ እስከ ፡ ለዓለም" ። ወተፈልጦቶሙስ ፡ በኅርየቶሙ ፡ በውስተ ፡ ዛቲ ፡ ሕይወት ፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ በእንቲአሆሙ ፡ "እሙንቱሰ ፡ እመ ፡ ትንሣኤ ፡ ኢያወስቡ ፡ ወኢይትዋሰቡ ፡ ዳእሙ ፡ ይከውኑ ፡ ከመ ፡ መላእክተ ፡ እግዚአብሔር" ። ወተመሰልዎ ፡ ለጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ዘይቤሎሙ ፡ ለሰብአ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ዘ፯ቱ ፡ በእንተ ፡ ኀዲገ ፡ አውስቦ ፡ "ወአንሰ ፡ አፈቅር ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ከማየ ፡ ወእብሎሙ ፡ ለእለ ፡ አልቦሙ ፡ አንስት ፡ ወሰዐቤራት ፡ ሠናይ ፡ ሎሙ ፡ ለእመ ፡ ነበሩ ፡ ከማየ ። ዘ፳ቱ ፡ ወሊተሰ ፡ ይመስለኒ ፡ ከመ ፡ ድንግልና ፡ ይኄይስ ፡ በእንተ ፡ እክየ ፡ ዘመን ፡ ይኄይሶ ፡ ለብእሲ ፡ ይንበር ፡ ከመዝ ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ አፈቅር ፡ ከመ ፡ ትንበሩ ፡ ዘእንበለ ፡ ኀዘን ። እስመ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ብእሲት ፡ ይሔሊ ፡ ለግብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘከመ ፡ እፎ ፡ ያሠምሮ ፡ ለእግዚአብሔር ። ወዘሰ ፡ ሎቱ ፡ ብእሲት ፡ ይሔሊ ፡ ለግብረ ፡ ዓለም ፡ በዘያሠምራ ፡ ለብእሲቱ ። እስመ ፡ ማእከለ ፡ ውሉባን ፡ ወደናግል ፡ ሀሎ ፡ ፍልጠት ፡ ክሙት ። ዘሰ ፡ ኢተወሰበት ፡ ለብእሲ ፡ ታስተሐምም ፡ በዘያቀርባ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወከመ ፡ ትኩን ፡ ንጽሕተ ፡ በሥጋሃ ፡ ወነፍሳ ። ዘሰ ፡ ባቲ ፡ ምት ፡ ታስተሐምም ፡ በንብረተ ፡

ዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የተረገመ ፡ ነው» የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ አለ ። ሌላውን ፡ ትእዛዝ ፡ በመፈጸም ፡ ምክንያት ፡ ትእዛዙን ፡ እፍርሰን ፡ እንዳንገኝ ፡ ከስንፍናችን ፡ ወገን ፡ የተነሣ ፡ ከሥራው ፡ ሁሉ ፡ እንጠበቅ ። ስለዚህ ፡ ገንዘባችንን ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ በጠብና ፡ በመጣሪያ ፡ የሚቀሙንን ፡ ሰዎች ፡ ዳግመኛ ፡ ልንጠላቸው ፡ አይገባንም ።

፲፻፺፯ አራተኛ ፡ ስለሚወሰኑበት ፡ ሁናቴ ፡ ይናገራል ። ይህችውም ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ስድስት ፡ ናት ። ከነርሱ ፡ መጀመሪያዋ ፡ ጋብቻን ፡ መተው ፡ ከነርሱም ፡ ፈጽሞ ፡ ያላገባ ፡ ከነርሱም ፡ ያገባ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከሚስቱ ፡ የተለየ ። መጀመሪያዎቹስ ፡ «ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ብለው ፡ ራሳቸውን ፡ ጃንደረባ ፡ ያደረጉ ፡ አሉ» (ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፲፪) ። ብሎ ፡ ጌታችን ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ የተናገረላቸው ፡ ናቸው ። ሁለተኞቹም ፡ «ስለእኔ ፡ ሚስቱን ፡ የተወ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ አለው» (ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፳፱-፴) ያለውን ፡ ቃሉን ፡ ተከተሉ ፡ ከዚች ፡ ሕይወት ፡ መለየታቸው ፡ በፈቃዳቸው ፡ ነው ። «እነርሱ ፡ ግን ፡ ከትንሣኤ ፡ በኋላ ፡ አያገቡም ፡ አይጋቡም ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መላእክት ፡ ይሆናሉ ፡ እንጂ» (ማቴ ፡ ፳፪ ፡ ፳፱-፴) ። ብሎ ፡ ጌታችን ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ እንደተናገረላቸው ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ። ጋብቻን ፡ ስለመተው ፡ ለቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ በ፯ኛው ፡ ክፍል ፡ እንዲህ ፡ ያላቸውን ፡ ሐዋርያውን ፡ ጳውሎስን ፡ መሰሉት ፡ «ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ እኔ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ እወዳለሁ ፡ ሚስት ፡ የሌላቸውንና ፡ ባልቴቶችንም ፡ እንደ ፡ እኔ ፡ ቢኖሩ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ እላቸዋለሁ ። በ፳ኛው ፡ ክፍል ፡ እኔስ ፡ ስለ ፡ ዘመን ፡ ችግር ፡ ድንግልና ፡ ይሻል ፡ ይመስለኛል ፡ ለሰው ፡ እንደዚህ ፡ ቢኖር ፡ ይሻለዋል ፡ ስለዚህ ፡ ያለኀዘን ፡ ልትኖሩ ፡ እወዳለሁ ። ሚስት ፡ የሌለችው ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንዴት ፡ ደስ ፡ በሚያሰኘው ፡ ገንዘብ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማገልገል ፡ ያስባልና ፡ ሚስት ፡ ያለችው ፡ ግን ፡ ሚስቱን ፡ ደስ ፡ በሚያሰኛት ፡ ገንዘብ ፡ ለዓለሙ ፡ ሥራ ፡ ያስባልና ፡ ባገቡትና ፡ ባላገቡት ፡ መካከል ፡ ግልጥ ፡ ልዩነት ፡ አለና ፡ ባል ፡ ያላገባች ፡ ሴት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚያቀርባት ፡ ገንዘብ ፡

ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ዘከመ ፡ እፎ ፡ ታሠምሮ ፡ ለምታ ። ወዘሂ ፡ ቀነየ ፡ ሕሊናሁ ፡ ወፈቀደ ፡ ከመ ፡ ይዕቀብ ፡ ድንግልናሁ ፡ ፈድፋደ ፡ ሠናየ ፡ ግብረ ፡ ገብረ ። ወለእመ ፡ ሞተ ፡ ምታ ፡ ለብእሲት ፡ ተግዕዘት ፡ ወብዕሰት ፡ ይእቲ ፡ ለእመ ፡ ነበረት ፡ በምክርየ ፤ እስመ ፡ ይመስለኒ ፡ ከመ ፡ ብየ ፡ መንፈሰ ፡ እግዚአብሔር ።

፫፻፶፪ ወዳግሚታኒ ፡ ጎዲግ ፡ አዝማድ ፡ ሥጋውያን ፡ ወጥሪታት፡ ወፍትወታተ ፡ ዓለም ፡ በከመ ፡ ነገርነ ፡ በዝንቱ ፡ ቅድመ ።

፫፻፶፫ ወሣልሲታኒ ፡ ነቢር ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ ወለቢሰ ፡ ሠቅ ፡ ወቀኒተ ፡ ሐቌ ፡ በአዲም ፡ በከመ ፡ ተጽሕፈ ፡ በእንተ ፡ ዮሐንስ ፡ መጥምቅ ።

፫፻፶፬ ወራብዒታኒ ፡ ጎዲገ ፡ መብልዐ ፡ ሥጋ ፡ ለዝሉፉ ፡ ወለእመ ፡ ኢረከበ ፡ ምክንያተ ፡ ግብር ፡ ለበትየ ፡ ወይን ። ወአቅልሎ ፡ ሲሲትኒ ፡ ዘእንበለ ፡ ከመ ፡ ተሠርዐ ፡ ለሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ወዘይመስሎ ።

፫፻፭ ወሐምሰኒ ፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ አኃው ፡ ጉቡአነ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ባስልዮስ ፡ በድርሳኑ ፤ በከመ ፡ ነፍስ ፡ አሐተ ፡ ወምክር ፡ አሐቲ ፡ ይኩኑ ፡ በሥጋቲሆሙ ። ወእመሰ ፡ ኮኑ ፡ ብዙኃነ ፡ በሥጋሆሙ ፡ ናሁ ፡ ኮነ ፡ መክብቦሙ ፡ ፩ዱ ፡ አምላክ ፡ አስተጋባኢሃ ፡ ለይእቲ ፡ ነፍስ ፡ አሐቲ ፡ ዘተጋብአት ፡ በማእሰረ ፡ ፍቅር ። ወኵሉ ፡ ለለአሐዱ፡ እምኔሆሙ ፡ ኢየሐዩ ፡ በርእሱ ፡ ባሕቲቱ ፤ ዳእሙ ፡ የሐይዉ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ለአሥምሮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይትቀነዩ ፡ ለለርእሶሙ ፡ በዕሪና ፡ ወፈቃድ ። ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ተኀድር ፡ ሰላም ፡ ማእከሌሆሙ ፤ ወኵሉ ፡ ለለ፩ዱ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ይትማሠጦ ፡ ለትሩፋት ፡ እምነ ፡ ካልኡ ፡ ወእልቦ ፡ በኀቤሆሙ ፡ ዘይትገፋዕ ። ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ይወርስዋ ፡ ለመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ወይትወሐድ ፡ ልቦሙ ፡ በውስተ ፡ ተአዝዞ ፡ ፍጹም ፡ ወየሐይዉ ፡ በከመ ፡ ሕይወት ፡ እንተ ፡ ትመጽእ ፡ በደኃሪ ፡ ዘመን ።

፫፻፭፮ ወሳድሲትኒ ፡ ዘይገብር ፡ ኵሎ ፡ ሕይወቶ ፡ ለጾም ፤ ወጸሎት ፡ ወጻማ ፡ ወተግባር ፡ ወአዝልፎተ ፡ ዝክረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአንብቦተ ፡ መጻሕፍቲሁ ፤ ወአእምሮ ፡ ትርጓሜሁ ፤ ወአንብቦ ፡



ትተጋለች ፤ በሥጋዋና ፡ በነፍሷም ፡ ንጽሕት ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ባል ፡ ያላት ፡ ሴት ፡ ግን ፡ ባሏን ፡ እንዴት ፡ አድርጋ ፡ ደስ ፡ በምታሰኘው ፡ ገንዘብ ፡ ለዚህ ፡ ዓለም ፡ አኗኗር ፡ ታስባለች ። ስውነቱን ፡ ገዝቶ ፡ ድንግልናውን ፡ ሊጠብቅ ፡ የወደደ ፡ ግን ፡ ፈጽሞ ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ሠራ ። ሴት ፡ ባሏ ፡ ቢሞት ፡ ነፃ ፡ ናት ፡ በምክሬም ፡ ብትኖር፡ ክብርት ፡ ናት ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ያደረብኝ ፡ ይመስለኛልና» ።

፫፻፶፪ ፪ተኛዋ ፡ ሥጋውያን ፡ ዘመዶችን ፡ ገንዘብንና ፡ የዓለምን ፡ ፈቃድ ፡ አስቀድመን ፡ እንደተናገርን ፡ መተው ፡ ነው ።

፫፻፶፫ ፫ኛዋም ፡ በገዳም ፡ መኖር ፡ ማቅ ፡ መልበስ ፡ ስለ ፡ ዮሐንስ ፡ መጥምቅ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ በዝናር ፡ ወገብን ፡ መታጠቅ ፡ ነው ።

፫፻፶፬ አራተኛዋ ፡ ለዘለዓለሙ ፡ ሥጋ ፡ መብላትን ፡ መተው ፡ ነው ። ወይን ፡ ለመጠጣት ፡ የግድ ፡ ምክንያት ፡ ባያገኘው ፡ ለቁመተ ፡ ሥጋና ፡ ለሚመስለውም ፡ ከታዘዘው ፡ በቀር ፡ ምግብን ፡ መቀነስ ፡ ነው ።

፫፻፭ አምስተኛ ፡ ባስልዮስ ፡ በድርሳኑ ፡ እንደተናገረ፡ ወንድሞች ፡ የተሰበሰቡ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ነፍስ፡ አንዲት ፡ ምክርም ፡ አንዲት ፡ እንደሆነች ፡ በሥጋቸው ፡ አንድ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። በሥጋቸው ፡ ብዙ ፡ ቢሆኑ ግን ፡ እነሆ ፡ በፍቅር ፡ ማሠሪያ ፡ የተሰበሰበች ፡ የአንዲቱ ፡ ማኅበር ፡ ሰብሳቢዋ ፡ አምላክ ፡ አንዱ ፡ አለቃቸው ፡ ሆነ ። ሁሉም ፡ ከነርሱ ፡ ወገን ፡ እያንዳንዱ ፡ በራሱ ፡ ብቻ ፡ አይኖርም ፡ በትክክልና ፡ በፈቃድ ፡ ለራሳቸው ፡ ይገዙ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይኖራሉ ፡ እንጂ ። ስለዚህ ፡ ሰላም ፡ በመካከላቸው፡ ታድራለች ። ሁሉም ፡ ከነርሱ ፡ እያንዳንዱ ፡ ከሌላው ፡ ትሩፋትን ፡ ይነጣጠቀዋል ፡ ከነርሱ ፡ ዘንድ ፡ የሚበደል ፡ የለም ። ስለዚህ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ይወርሷታል ፡ በፍጹም ፡ ትእዛዝ ፡ ልባቸው ፡ አንድ ፡ ይሆናል ፡ በኋላ ፡ ዘመን ፡ እንደምትመጣው ፡ ሕይወት ፡ ይኖራሉ ።

፫፻፭፮ ስድስተኛዋ ፡ ሕይወቱን ፡ ሁሉ ፡ ለጾም ፡ ለጸሎት ፡ ለድካም ፡ ለሥራ ፡ የሚያደርግ ፡ ዘወትርም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማሰብ ፡ መጻሕፍትን ፡ ለማንበብ ፡ ትርጓሜውን ፡ ለማወቅ ፡ ወዳጆቹን፡

ገድላቲሆሙ ፡ ለቅዱሳኒሁ ፡ ለተመስሎቶሙ ፡ ለፍቁራኒሁ ። ወእንዘ ፡ ይሔልዩ ፡ ፍጻሜ ፡ እካላቲሁ ፡ ወዕበየ ፡ ግብራቲሁ ፡ ወውጣኔሁ ፡ ወሠናየ ፡ ሥነ ፡ ፍጡራኒሁ ፡ ወተእኅዞታ ፡ በእሐተ ፡ ሀላዌ ፡ ግብሩ ፡ ዘኢትፀራዕ ፡ ወዕጻበ ፡ ምግብናሁ ፡ ሎሙ ፡ እንዘ ፡ ይከልእዎ ፡ በዝንቱ ፡ ለሥጋሆሙ ፡ እምኵሉ ፡ ዘያወፅእ ፡ እምግብረ ፡ ተእዝዞ ፤ ወእንዘ ፡ የዓቅቡ ፡ ልሳናቲሆሙ ፡ እምኵሉ ፡ ነገር ፡ ዘእልቦ ፡ በቍዔት ፡ ኢ ፡ ለነባቢሁ ፡ ወኢ ፡ ለዘይሰምዖ ። ወሕዋሳቲሆሙ ፡ እንተ ፡ አፍኣ ፡ የአኀዙ ፡ ከመ ፡ ኢያብጽሑ ፡ ኀበ ፡ ነፍሶሙ ፡ ዘኢይደሉ ፡ ለሐልዮ ፡ ወለነጊር ፡ ዘእንበለ ፡ ምግባር ፡ ሠናይ ፡ ወሕዋሳቲሆሙኒ ፡ እንተ ፡ ውስጥ ፡ ይዕቅቡ ፡ እንተ ፡ ትሔሊ ፡ ባቲ ፡ ወትትሜሰል ፡ አው ፡ በተዘክሮ ፡ አው ፡ በሐልዮ ፡ አው ፡ በተዓቅቦ ፡ ካልእ ፡ ዘእንበለ ፡ በዘቀደመ ፡ ዝክሩ ።

፫፻፳፬ ኃምስ ፡ በእንተ ፡ ሊቀ ፡ ምኔት ፡ ወረድኡ ፡ ወኵሎሙ ፡ ሕዝብ ፡ ወመጋቢ ፡ ወዐቃቢ ፡ አንቀጽ ፡ ዘኒቅያ ፡ ፸ወ፰ቱ ፡ ወኢይኅረዩ ፡ መነኮሳተ ፡ ምኔት ፡ ሊቀ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ዘእንበለ ፡ በትእዛዘ ፡ ኮሬ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወለእመ ፡ አዘዘ ፡ ወሤመ ፡ ሊቀ ፡ ምኔት ፡ በሕይወቱ ፡ ካልአ ፡ ብእሴ ፡ ይኩን ፡ ሊቀ ፡ ላዕለ ፡ ምኔት ፡ እምድኅሬሁ ፡ ዘኢኮነ ፡ እምዘመዱ ። እላ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ፈቀደ ፡ ሊቅ ፡ መዋቲ ፡ ሠናየ ፡ ሃይማኖት ፡ እምካልእኒሁ ፡ ወኅርየቱ ፡ ኪያሁ ፡ ይኩን ፡ ከመዝ ፡ ዘቦቱ ፡ በቍዔተ ፡ ምኔት ፡ ወንጽሕ ፡ ወፈሪሃ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወጽኑዐ ፡ እምነውር ፡ ይኩን ፡ ሊቀ ፡ በከመ ፡ አዘዘ ፡ ቦቱ ፡ ዘሞተ ፡ ወዝንቱ ፡ አንቀጽ ፡ ዘእንበለ ፡ ግዘት ።

፫፻፳፭ ዘኒቅያ ፡ ወኢይኩን ፡ ሊቀ ፡ ላዕለ ፡ ምኔት ፡ ዘእንበለ ፡ ዘልህቀ ፡ ውስቴታ ፡ ወዘየአምር ፡ ሕጋጋቲሃ ፡ ወዘቦቱ ፡ ገድል ፡ በውስተ ፡ ምንኵስና ፡ ወዘኢኮነ ፡ ዐብደ ፡ ወኢድኩመ ፡ ምክር ፡ ወዘኢተአምረት ፡ ቦቱ ፡ አበሳ ፡ ውስተ ፡ ምኔት ፡ ወኢ በአፍኣ ፡ እምኔሃ ፡ ወዘኮነ ፡ ሠናየ ፡ ግእዝ ፡ ምሁረ ፡ ወዐቃቤ ፡ ቀኖና ፡ ሕጋዊት ፡ ለባዌ ፡ ዘይመጽእ ፡ ውስቴቱ ፡ ወይቀውም ፡ በተደልዎ ፡ ወዘኮነ ፡ መሥመረ ፡ ለዘሚኖ ፡ ወዘኮኑ ፡ ሎቱ ፡

ለመምሰል ፡ የቅዱሳኖቹን ፡ ገድል ፡ ለማንበብ ፡ የሚያደርግ ፡ ነው ። የእካሉን ፡ ፍጹምነት ፡ የሥራውንም ፡ ታላቅነት ፡ አጀማመሩን ፡ የፍጡሮቹን ፡ ውበት ፡ ማማር ፡ የማትጓደል ፡ ሥራው ፡ በአንዲት ፡ አኗኗር ፡ መያዙን ፡ የእነርሱን ፡ መጠበቅ ፡ ጭንቀት ፡ እያሰቡ ፡ ከመታዘዝ ፡ ሥራ ፡ ወገን ፡ ከሚያወጣው ፡ ሁሉ ፡ ሥጋቸውን ፡ በዚህ ፡ እየከለከሉ ፡ ለሚናገረው ፡ ለሚሰማውም ፡ ጥቅም ፡ ከሌለው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አንደበታቸውን ፡ እየጠበቁ ፡ ከበጎ ፡ ሥራ ፡ በቀር ፡ ለማሰብና ፡ ለመናገር ፡ የማይገባውን ፡ ወደሰውነታቸው ፡ እንዳያደርሱ ፡ አፍአዊ ፡ ሰውነታቸውን ፡ ይይዙ ፡ ዘንድ ፡ ውስጣዊ ፡ ሰውነታቸውንም ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ የምታስብበትን ፡ የምትመስልበትንም ፡ በመሻት ፡ ወይም ፡ በማሰብ ፡ ወይም ፡ አስቀድሞ ፡ ከተነገረው ፡ በቀር ፡ በሌላ ፡ እጠባበቅ ፡ ይጠብቁ ።

፫፻፳፬ አምስተኛ ፡ ስለገዳሙ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ስለ ፡ ረድኡ ፡ ስለማኅበሩም ፡ ሁሉ ፡ ስለመጋቢውና ፡ ስለ ፡ በር ፡ ጠባቂውም ፡ ይናገራል ። ኒቅያ ፡ ፸፰ ፡ የገዳም ፡ መነኮሳት ፡ ያለ ፡ ቆሞስ ፡ ትእዛዝ ፡ በላያቸው ፡ ላይ ፡ መምህር ፡ አይሹሙ ። ከርሱ ፡ በኋላ ፡ ለገዳሙ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ የገዳሙ ፡ አስተዳዳሪ ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ አዝዞ ፡ ቢሾም ፡ ከዘመዶቹ ፡ ወገን ፡ ያይደለው ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ የገዳም ፡ መምህር ፡ ይሁን ። እርሱን ፡ መምረጡ ፡ ከባልንጀሮቹ ፡ ይልቅ ፡ ሃይማኖቱ ፡ ያማረ ፡ የሚሞተው ፡ አስተዳዳሪ ፡ ፈቃድ ፡ ቢሆን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እርሱንም ፡ መምረጡ ፡ እንደዚህ ፡ ይሁን ፡ ለገዳሙ ፡ ጥቅም ፡ ያለው ፡ ንጽሕና ፡ ያለው ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፡ ከነውር ፡ ንጹሕ ፡ የሆነው ፡ ሟቹ ፡ እንዳዘዘለት ፡ አስተዳዳሪ ፡ ይሁን ፡ ይህ ፡ ያልተወገዘበት ፡ አንቀጽ ፡ ነው ።

፫፻፳፭ ኒቅያ ፡ በውስጧ ፡ ያደገ ፡ ሕግጋቷንም ፡ ያወቀ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በገዳሙ ፡ ላይ ፡ አስተዳዳሪ ፡ አይሁን ፡ በምንኩስናው ፡ ገድል ፡ ያለው ፡ ሰነፍ ፡ ምክርን ፡ የማያውቅ ፡ በገዳሙ ፡ ውስጥ ፡ ከርሷም ፡ በውጭ ፡ በደል ፡ ያልተገኘበት ፡ ጠባዩ ፡ ያማረ ፡ የሆነ ፡ የተማረ ፡ የሕግን ፡ መንገድ ፡ ጠባቂ ፡ በራሱ ፡ የሚመጣውን ፡ አስተዋይ ፡ በመዘጋጀት ፡ የሚኖር ፡ የሾመውን ፡ ወዳጅ ፡ የሆነ ፡ ያለ ፡ ክርክርና ፡ ያለመለያየት ፡

በምዐ ፡ ጉባኤ ፡ መንኰሳት ፡ በዝንቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ተጋእዞ ፡ ወፍልጠት ፡ ይኩን ፡ ማእከሌሆሙ ፡ በዝንቱ ፡ ወይረበይዎ ፡ ሊቀ ።

፫፻፳፬ ሀሰ ፡ ወሊቀ ፡ ምኔት ፡ ይኩኖሙ ፡ ለእኀው ፡ ከመ ፡ እብ ፡ ጠባይዓዊ ፡ ምበለ ፡ ውሉዱ ፡ እለ ፡ ይትኤዘዙ ። ወከመ ፡ መምሀራን ፡ ሥጋውያን ፡ ምስለ ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡ ታሕተ ፡ እደዊሆሙ ፡ እስመ ፡ እብ ፡ ያፈቅር ፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ ውሉዱ ፡ ሠናያን ፡ ወጠቢባን ፡ ወኀፋርያን ፡ ወትሑታን ። እስመ ፡ ክብረ ፡ ውሉድ ፡ ትበቍዕ ፡ ለአበዊሆሙ ። ወክማሁ ፡ መምሀራንኒ ፡ ይፈቅዱ ፡ ከመ ፡ ይኩኑ እርዳኢሆሙ ፡ ሠናያን ፡ እእምሮ ፡ ወምግባር ፡ ወተመሃርያን ፡ ውበተ ፡ ኪነታቶሙ ፡ ወይኩኑ ፡ ተመሃርያን ፡ ትሩፋነ ፡ ወመዋዕያን ፡ ለዘይትቃወሞሙ ፡ ወበእንቲአሆሙ ፡ ይትእኰቱ ፡ መምሀራኒሆሙ ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ጽድቅ ፡ ይበጽሕ ፡ በፍጻሜ ፡ ተልእኮቶሙ ።

፫፻፳፭ ወይደልዎ ፡ ለእብ ፡ መንፈሳዊ ፡ ወመምሀረ ፡ ግብራት ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ፈቃዱ ፡ ወኀሠሣሁ ፡ ለደቂቁ ፡ ተመሃርያን ፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ ተመሃርያን ፡ ትሑታን ፡ ወጠቢባን ፡ ሠናያን ፡ ወጻሐቅያን ፡ ውበተ ፡ ተፀምዶ ፡ ወመዋዕያን ፡ ለዕድዋኒሆሙ ፡ መንፈሳውያን ፡ ከመ ፡ ይንሥኡ ፡ እክሊላተ ፡ በብሐት ፡ እምክርበቶስ ፡ ዘረበዮሙ ፡ ለእግብርቲሁ ፡ ጻሐቅያን ፡ ለሠናይ ፡ ወቅሩባን ፡ ኀቤሁ ፡ ወመፍቀርያን ፡ ሎቱ ፡ ወገባርያን ፡ ፈቃዶ ።

፫፻፳፮ ወይደልዎ ፡ እምኔሆሙ ፡ ፍጻሜ ፡ ክብር ፡ በእንተ ፡ ዘረሰዮሙ ፡ በትምህርቱ ፡ እኀወ ፡ ለእግዚእነ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ በትምህርቱ ፡ ርኁብት ፡ ይቤ ፡ "እስመ ፡ ኵሉ ፡ ዘይገብር ፡ ፈቃዶ ፡ ለአቡየ ፡ ውእቱ ፡ እኁየ" ። እመሰ ፡ ኢኮኑ ፡ ርቱዓነ ፡ በእምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ኮነ ፡ ይሜግቦሙ ፡ በእኩይ ፡ ወኢይሜግቦሙ ፡ በሠናይ ፡ ይትኀፈር ፡ በዕለተ ፡ ደይን ። ወበዝንቱ ፡ ዘመን ፡ ለእመ ፡ ኮኑ ፡ ውሉድ ፡ እኩያን ፡ ወውእቶሙ ፡ በእምሳለ ፡ ሕምዛት ፡ ዘይወድዩ ፡ ቅድመ ፡ ሕምዛቲሆሙ ፡ ላዕለ ፡ ወላድያኒሆሙ ።

፫፻፳፯ ወበእንተዝ ፡ ይደልዎ ፡ ለኖላዊ ፡ ከመ ፡ ይመግቦሙ ፡ በዘይደሉ ፡ ወበዘይትፈቀድ ፡ ለለ፩ ፡ ፩ዱ ፡ በእምጣነ ፡ ሐሳበ ፡ መዋዕሊሆሙ ፡ ለዘቀ



የተሰበሰቡ ፡ መነኰሳት ፡ በዚህ ፡ ምስክር ፡ የሆኑት ፡ በዚህ ፡ በመካከላቸው ፡ ይሁን ፡ እበተዳዳሪም ፡ ያድርጉት ።

፫፻፳፬ በስ ፡ እበ ፡ ምኔቱ ፡ ሥጋዊ ፡ እባት ፡ ለሚታዘዙት ፡ ልጆቹ ፡ እንደሚያደርግላቸው ፡ ሥጋውያን መምሀራንም ፡ ከሥልጣናቸው ፡ በታች ፡ ላሉት ፡ እንደሚያደርጉላቸው ፡ ለወንድሞች ፡ ያድርግላቸው ። አባት ፡ ልጆቹ ፡ መልካሞችና ፡ እዋቂዎች ፡ የሚፈሩና ፡ ትሑቶች ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ይወዳልና ፡ የልጆች ፡ ክብር ፡ ወላጆቻቸውን ፡ ትጠቅማለችና ፡ እንደዚሁም ፡ መምሀራን ፡ ደቀመዛሙርቶቻቸው ፡ በዕውቀትና ፡ በሥራ ፡ እውነተኞች ፡ ጥበባቸውን ፡ የተማሩ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ይወዳሉ ። ተማሪዎቹም ፡ ፍጹማን ፡ የሚቃወማቸውን ፡ ድል ፡ የሚነሱ ፡ ይሁኑ ። በእነርሱ ፡ መምሀራኖቻቸው ፡ ይመሰገናሉ ። ይህ ፡ እውነት በአገልግሎታቸው ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ይደርሳልና ።

፫፻፳፭ ለሥራዎች ፡ መምሀርና ፡ ለመንፈሳዊ ፡ እባት ፡ ይገባዋል ። ይህችውም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሥራናት ፤ ለሚማሩት ፡ ልጆቹ ፡ ፈቃዱና ፡ ፍላጎቱ ፡ የተማሩ ፡ ትሑቶች ፡ አዋቂዎች ፡ መልካሞች ፡ በተባሕትዎ ፡ የተጉ ፡ ረቂቃን ፡ ባላጋሮቻቸውን ፡ ድል ፡ የሚነሱ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ እገልጋዮቹ ፡ ለበጎ ፡ ሥራ ፡ ትጉሖች ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ እንዲቀርቡ ፡ እርሱን ፡ እንዲወዱ ፡ ፈቃዱን ፡ እንዲፈጽሙ ፡ ካደረጋቸው ፡ ከክርበቶበ ፡ የምስጋና ፡ አክሊሎችን ፡ ይቀዳጁ ፡ ዘንድ ።

፫፻፳፮ በትምህርቱ ፡ የጌታችን ፡ ወንድሞች ፡ በሳደረጋቸው ፡ ከነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ፍጹም ፡ ክብር ፡ ይገባዋል ፡ እርሱ ፡ በማትወሰን ፡ ትምህርቱ ፡ እንዲህ ፡ ብሏልና ፡ «የእባቴን ፡ ፈቃድ ፡ የሚያደርግ ፡ ሁሉ ፡ እርሱ ፡ ወንድሜ ፡ ነውና» (ማቴ ፡ ፲፪ ፡ ፶) ። እግዚአብሔርን ፡ በማምለክ ፡ የቀኑ ፡ ካልሆኑ ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ በክፉ ፡ እጠባበቅ ፡ እንጂ ፡ በበጎ ፡ እጠባበቅ ፡ አይጠብቃቸውምና ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ያፍራል ። በዚህ ፡ ዘመን ፡ ልጆቻቸው ፡ ክፉዎች ፡ ቢሆኑ ፡ በወላጆቻቸው ፡ ላይ ፡ መርዛቸውን ፡ እስቀድመው ፡ በሚጥሉ ፡ በመርዞች ፡ አምሳል ፡ ናቸው ።

፫፻፳፯ ስለዚህ ፡ ጠባቂው ፡ እያንዳንዱን ፡ በሚገባ ፡ በሚወደድ ፡ ገንዘብ ፡ ሊጠብቃቸው ፡ ይገባል ። በመታዘዛቸው ፡ ለቀደመውና ፡ ለኋለኛው ፡ እንደ

ይሙ ፡ ወለዘተድኅረ ፡ ውስተ ፡ ትእዛዘሙ ፡ ወዘወስከሂ ፡ ወአሕጽጾ ፡ ውስተ ፡ ጾምዎቶሙ ፡ ወዘይትኪምሂ ፡ ወዕረፍት ፡ ውስተ ፡ ተማህሮሙ ፡ ወዘሰበይሂ ፡ ወበናእስ ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋሆሙ፡ ለቀረብሂ ፡ ወርሒቅ ፡ እምግብረተ ፡ ልማዳተ፡ ሆሙ ፡ በጥዒናሂ ፡ ወበደዌ ፡ ውስተ ፡ ፍጥረ ቶሙ ።

፫፻፶፰ ወኢኮነ ፡ ፩ደ ፡ ቀኖናሁ ፡ ለዝንቱ ፡ ተፈልጠ ፡ ዘብሔረ ፡ ለመሀብት ፡ ከመ ፡ ይሥርዑ ፡ ኮሎ ፡ ለለ፩፩ ፡ ፩፩ ፡ በኮሉ ፡ ጊዜ ፡ በዘይደሉ ፡ ሎቱ ፡ አንዘ ፡ ይፈጽምዎን ፡ ዘጽሑፍ ፡ ዘይብል ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ኮኑ ፡ ይሁቡ ፡ ለኮሉ ፡ ለሰ፩፩ ፡ ፩፩ ፡ ዘይፈቅዶ ፡ ባሕቱ ፡ ዛቲ ፡ አርአያ ፡ አሐቲ ፡ ተኩን ፡ ለኮሎሙ ፡ ወይእቲ ፡ ከመ ፡ ኢይብ ልዑ ፡ ለግሰም ፡ ወኢበስስሰት ፡ ወበእንተ ፡ ከመ ፡ እስ ፡ ታሕተ ፡ እዴሁ ፡ ስሊቅ ፡ ይትመስ ልዎ ፡ ሎቱ ፡፡ ወይደሉ ፡ ከመ ፡ ትኩን ፡ ሐረተ ፡ ፍጻሜተ ፡ በኮሉ ፡ ትእዛዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ኢይትሐዘብ ፡ ፩፩ሂ ፡ እምኔሆሙ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ እንበለ ፡ ክሂል ፡ ከመ ፡ ይዕቀብ ፡ ትእ ዛዘ ፡ እግዚአብሔር ፡፡ ወይደሉ ፡ ከመ ፡ ትኩን ፡ አርአያሁ ፡ ወማብሩ ፡ በጊዜ ፡ አርምሞቱ ፡ ዘይበ ቍዖሙ ፡ ፈድፋደ ፡ እምዘይሜህሮሙ ፡ በቃሉ ፡ ወይተሐት ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ኮሬ ፡ ኤጲስቆጶስ ።

፫፻፶፱ ዘኒቅያ ፡ ወይደሉ ፡ ሰሊቀ ፡ ምኔት ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ረድኡ ፡ ወላእኩ ፡ ዘይቀውም ፡ ቅድመ ፡ ገጹ ፡ አስተማሳሌ ፡ በነፋሱ ፡ ግብረ ፡ ኤልሳዕ ፡ ነቢይ፡፡ እስመ ፡ እንዘ ፡ ውእቱ ፡ ወልደ ፡ ፩ዱ ፡ ብእሲ ፡ ነበረ ፡ እምዓበይተ ፡ እስራኤል ፡ ኢኀረረ ፡ እምተልእኮተ ፡ ኤልያስ ፡ ነቢይ ፡ ወውእቱ ፡ ፩ዱ ፡ ብእሲ ፡ እምእለ ፡ የኀድሩ ፡ በብሔረ ፡ ገለዓድ ፡፡ ወኢይቤ ፡ በልቡ ፡ እፎ ፡ እትለአክ ፡ ለዝንቱ ፡ ቀረናዊ ፡ ወእመጽእ ፡ ማእከለ ፡ ማኅ ደሪሆሙ ፡ ለደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ኀዘ ፡ እለ ፡ የአ ምሩኒ ፡ ወእትለአክ ፡ ለብእሲ ፡ ፈላሲ ፡ ወምስ ኪን ፡ እላ ፡ ኮነ ፡ ይሬኢ ፡ ከመ ፡ ይእቲ ፡ ሀገር ፡ እንተ ፡ ይንሶሱ ፡ ባቲ ፡ መምህሩ ፡ ኢይደልዎሙ ለሰብእ ፡ ዚአሃ ፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ ሎቱ ፡ ላእካነ ወኢአርድእተ ፡ ወዘከመ ፡ ዛቲ ፡ ሕሊና ፡ ይደ ልዎሙ ፡ ለአርድእት ፡ ከመ ፡ የሐልዩ ፡ ወለእመኒ ፡ ኮኑ ፡ በክብረ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ክቡራነ ፡ እመምህ ራኒሆሙ ፡፡ ወይደሉ ፡ ከመ ፡ ይበሉ ፡ በልቦሙ ፡ ወይ ፡ ለነ ፡ በእንተ ፡ ዘኮነ ፡ ዘኢንክል ፡ ከመ ፡



ዘመናቸው ፡ ሐሳብ ፡ መጠን ፡ በድካማቸው ፡ ጊዜ ፡ በማብዛትና ፡ በማሳነስ ፡ በሥራቸውም ፡ ጊዜ ፡ በድካምና ፡ በዕረፍት ፡ በማብዛትና ፡ በማ ሳነስ ፡ በሕይወተ ፡ ሥጋቸው ፡ ከልማዳቸው ፡ ሥራዎች ፡ ስማቅረብና ፡ ለማራቅ ፡ በሰውነታ ቸው ፡ ውስጥ ፡ በጤናና ፡ በደዌ ።

፫፻፶፰ የዚህ ፡ የመሰየት ፡ ሕጉ ፡ አንድ ፡ አይደለም ፡ ሹማምቱ ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ሁልጊዜ ፡ የሚገባ ውን ፡ ማዘዝ ፡ ይገባቸዋል ። እነሱ ፡ ለእያንዳ ንዱ ፡ የሚፈልገውን ፡ ይሰጡ ፡ ነበርና ፡ የሚ ሰውን ፡ ጽሑፍ ፡ እየፈጸሙ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ይህች አብነት ፡ ለሁላቸው ፡ ትሁናቸው ። ይህችውም ፡ የጣመ ፡ እንዳይበሉ ፡ እየሳሱም ፡ እንዳይበሉ ፡ ከሥልጣኑ ፡ በታች ፡ ያሉት ፡ አስተዳዳሪውን ፡ ይምሰሉት ። በእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ሁሉ ፡ አካሄዱ ፡ ፍጽምት ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ይጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ እርሱ ፡ ያለ ፡ ችሎታ ፡ እንዳይሆን ፡ ከእነርሱ ፡ ወገን ፡ አንዱስ ፡ እንኳ ፡ እንዳይጠራጠር ፡ በብ ሕትውናው ፡ ጊዜ ፡ በአብነትነቱና ፡ በሥራው ፡ ፈጽሞ ፡ በቃሉ ፡ ከሚያስተምራቸው ፡ ወገን ፡ የሚጠቅማቸው ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ፡ ቆሞሱ ፡ ለኤጲስቆጶሱ ፡ ይታዘዝ ።

፫፻፶፱ ኒቅያ ፡ የገዳሙ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ረድኡ ፡ በፊቱ ፡ የሚቆመው ፡ አገልጋዩ ፡ በሰውነቱ ፡ የነቢዩ ፡ የኤልሳዕን ፡ ሥራ ፡ የሚያስመስል ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ፡ ከእሥራኤል ፡ ውስጥ ፡ ከታላላቆቹ ፡ ወገን ፡ የአንዱ ፡ ክቡር ፡ ልጅ ፡ ሲሆን ፡ ኤልያ ስን ፡ ከማገልገል ፡ አላረፈምና ፡ ይኸውም ፡ በገ ለዓድ ፡ ከሚኖሩት ፡ አንዱ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ቀሬ ናዊ ፡ እንዴት ፡ አገለግለዋለሁ ፡ በሚያውቁኝ ፡ በእሥራኤል ፡ ቤት ፡ መካከል ፡ እንዴት ፡ እመ ጣለሁ ። ለስደተኛውና ፡ ለመጻተኛው ፡ ሰው ፡ እንዴት ፡ አገለግለዋለሁ ፡ አላለም ። መምህሩ ፡ የሚመላለስበት ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ አገልጋዮቹና ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ መሆን ፡ እንዳልተገባቸው ፡ ያይ ፡ ነበር ፡ እንጂ ። ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ እንደ ዚህች ፡ ያለች ፡ ሐሳብ ፡ ሊያስቡ ፡ ይገባቸዋል ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ክብር ፡ ከአዋቂ ዎቻቸው ፡ ይልቅ ፡ የከበሩ ፡ ቢሆኑ ፡ በሥጋ ፡ የወለዱን ፡ አባቶቻችን ፡ በእሳደጉን ፡ ፈንታ ፡ የምናገለግላቸው ፡ ከሆነ ፡ መንፈሳውያን ፡ አባ

ንፍድዮሙ ፡ ለአበዊነ ፡ እለ ፡ ወለዱነ ፡ በሥጋ ፡ ህየንተ ፡ ዘሐፀኑነ ፤ እሮ ፡ ፈድፋደ ፡ ይደልወነ ፡ ከመ ፡ ንፍድዮሙ ፡ ለአበዊነ ፡ መንፈሳውያን ።

፫፻፸ ወይደልዎሙ ፡ ለሊቃውንት ፡ ከመ ፡ ይግበሩ ፡ ለአርዳኢሆሙ ፡ ተአዛዝያን ፡ በከመ ፡ ኮነ ፡ ኢዮብ ፡ ይገብር ፡ በበነግህ ፡ ኵሎ ፡ ዕለተ ፡ ያቄርብ ፡ ቍርባነ ፡ በእንተ ፡ ብእሲቱ ፡ ወውሉዱ ፡ ወላእካኒሁ ። ወከመዝ ፡ ይደሉ ፡ ሎሙ ፡ ለመምህራን ፡ ይግበሩ ፡ ከማሁ ፡ እንዘ ፡ ይጼልዩ ፡ ለአርድእቲሆሙ ፤ ወይሰአልዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሐሪ ፡ ምሕረተ ፡ በእንተ ፡ እድኅኖቶሙ ፡ ወዝንቱ ፡ እንቀጽ ፡ ዘእንበለ ፡ ግዘት ።

፫፻፸፩ ወይርአይ ፡ ሊቀ ፡ ምኔት ፡ እምአኃው ፡ ኀበ ፡ ዘሎቱ ፡ ምግባር ፡ ሠናይ ፡ ዘይፈርህ ፡ እምዕለተ፡ ኰንኔ ፤ ወመፍቀሬ ፡ ለኂሩተ ፡ ምኔት ፡ ወይረስዮ ፡ ቀዋሜ ፡ ላዕለ ፡ ምኔት ፡ ወላዕለ ፡ መዛግብቲሁ ፡ ከመ ፡ የሐውጾሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ አኃው ። ወዘይረውፅ ፡ ውስተ ፡ መፍቅዳቲሆሙ ፡ ወዘኢየኀሪ ፡ ዐቢየ ፡ ፈድፋደ ፡ እምንኡስ ፡ ወኢይትዐዶ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዘአመገቦ ፡ሎቱ ።

፫፻፸፪ ወይኩን ፡ ኅሩየ ፡ ወንጹሐ ፡ ወምእመነ ፡ እኩ ፡ እኩየ ፡ ወኢፈታዌ ፡ ወኢያጥሪ ፡ ምንተኒ ። ወኢይብላዕ ፡ ወኢይስተይ ፡ ወኢይኑም ፡ ውስተ ፡ በዓተ ፡ ፩ዱ ፡ ዘቦቱ ፡ ንዋር ። ወኢይኅረይ ፡ ፩ደ ፡ እምአዝማዲሁ ፡ ወፍቁራኒሁ ፡ በምንትኒ ፡ ለግብረ ፡ ምኔት ። አላ ፡ ይግበር ፡ በዘይሴባሕ ፡ ቦቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንቲአሁ ፤ ከመ ፡ ይትፈጸም ፡ በላዕሌሁ ፡ ቃሉ ፡ ዘይብል ፡ "ብፁዕ ፡ ውእቱ ፡ ገብር ፡ ዘመጺአ ፡ እግዚኡ ፡ ይረክቦ ፡ እንዘ ፡ ይገብር ፡ ኵሎ ፡ ዘአዘዞ ፡ ሎቱ" ፡ ወከመ፡ ይኩን ፡ መጋቤ ፡ ንዋይ ፡ ዘምኔት ፡ ምእመነ ፡ ወምኩረ ፡ በዘይሁብ ፡ እምዘተአመነ ፡ ቦቱ ፡ በፍሡሕ ፡ ገጽ ፡ ወበልብ ፡ ንጹሕ ፡ ሰላማዊ ፡ ዘይሔውጾሙ ፡ ለድኩማን ፡ ወይፌጽም ፡ ጻሕቆሙ ፡ ለድዉያን ፤ ወኢይኩን ፡ መፍቀሬ ፡ ዕረፍት ፡ ወበሊዕ ፡ ወሰትይ ፡ ባሕቲቱ ፡ ዘእንበለ ፡ አኃዊሁ ፡ ዲበ ፡ ማእድ ፡ ዘማእከል ፡ ዕጉቅ ፡ በኀበ ፡ ኵሎሙ ፡ ወኢያቅልል ፡ አሐደሂ ፡ እምእለ ፡ ይመጽኡ ፡ ኀበ ፡ ምኔት ። ዳእሙ ፡ ያክብሮሙ ፡ በዘሀለወ ፡ ኀቤሁ ። ወየሐውጾሙ ፡ በዘቦ ፡ እመዛግብተ ፡ ምኔት ፡ እመብልዕ ፡ እንተ ባቲ ፡ ይከውን ፡ ላዕሌሃ ፡ ሙስና ፡ ወኀፍረት ፡



ቶቻችንንማ ፡ እናገለግላቸው ፡ ዘንድ ፡ እንዴት ፡ ይገባን ፡ ይሆን ? ያልቻልን ፡ ስለሆነ ፡ በልቡናቸው ፡ ወዮልን ፡ ማለት ፡ ይገባቸዋል ።

፫፻፸ ሁልጊዜ ፡ በነግህ ፡ በነግህ ፡ በለሚስቱ ፡ ስለ ልጆቹ ፡ ስለአገልጋዮቹ ፡ መሥዋዕት ፡ ይሠዋ ፡ እንደነበረ ፤ እንደ ፡ ኢዮብ ፡ መምህራንም ፡ ለሚታዘዙ ፡ ደቀመዛሙርቶቻቸው ፡ ማድረግ ፡ ይገባቸዋል ። እንደዚህ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቶቻቸው ሊጸልዩ ፡ እነርሱን ፡ በለማዳን ፡ የምሕረት ፡ ባለቤት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሲለምኑ ፡ መምህራን ፡ እንዲህ ፡ ማድረግ ፡ ይገባቸዋል ፡ ይህ ፡ አንቀጽ፡ ያልተወገዘበት ፡ አንቀጽ ፡ ነው ።

፫፻፸፩ የገዳሙ ፡ አበተዳዳሪ ፡ ከወንድሞች ፡ ወገን ፡ ከፍርድ ፡ ቀን ፡ የተነሣ ፡ የሚፈራውን ፡ በጎ ፡ ምግባር ፡ ያለውን ፡ ገዳሙ ፡ የሚጠቀምበትን ፡ የሚወድ ፡ በዕቃ ፡ ቤቱም ፡ ላይ ፡ ወንድሞችን ፡ ሁሉ ፡ የሚኀበኛቸውን ፡ ለመርዳት ፡ የሚፋጠነውን ፤ ፈጽሞ ፡ ከትንሽ ፡ ይልቅ ፡ ትልቁን ፡ የማይመርጠውን ፡ በሾመው ፡ ገንዘብ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ የማይተላለፈውን ፡ ይመርምር ።

፫፻፸፪ የተመረጠ ፡ ንጹሕ ፡ የታመነ ፡ ይሁን ፤ ክፉ ፡ ገንዘብ ፡ ወዳጅ ፡ ያይደለ ፡ ይሁን ፤ ምንም ፡ ገንዘብ ፡ አያጠራቅም ፡ ብቻውን ፡ አይብላ ፡ አይጠጣ ፡ ነውር ፡ ባለበት ፡ በአንዱ ፡ ቦታ ፡ ውስጥ ፡ አይደር ፡ ከዘመዶቹ ፡ ከወዳጆቹ ፡ ወገን ፡ አንዱን ፡ በምንም ፡ ለገዳሙ ፡ ሥራ ፡ አይምረጥ ፡ «ጌታው ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ያዘዘውን ፡ ሲያደርግ ፡ የሚያገኘው ፡ ባሪያ ፡ ብፁዕ ፡ ነው» ፡ (ማቴ ፡ ፳፬ ፡ ፵፮) ። ያለው ፡ ቃሉ ፡ በርሱ ፤ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚመሰገንበትን ፡ ይሥራ ፡ እንጂ ፤ የገዳሙ ፡ ገንዘብ ፡ ሹም ፡ የታመነ ፡ የተፈተነ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ከታመነበት ፡ ወገን ፡ በሚሰጥ ፡ ገንዘብ ፡ ደስታ ፡ ባለው ፡ ገጽ ፡ ሰላማዊ ፡ በሆነ ፡ በንጹሕ ፡ ልብ ፡ ደካሞቹን ፡ የሚኀበኛቸው ፡ የድሆችንም ፡ ግዳጃቸውን ፡ የሚፈጽምላቸው ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ዕረፍትን ፡ የሚወድ ፡ አይሁን ። ነገር ፡ ግን ፡ በሁሉም ፡ ዘንድ ፡ በታወቀው ፡ ማዕድ ፡ መካከል ፡ ያለወንድሞቹ ፡ ብቻውን ፡ የሚበላና ፡ የሚጠጣ ፡ አይሁን ፤ ወደገዳሙ ፡ ከሚመጡት ፡ ወገን ፡ አንዱንስ ፡ እንኳ ፡ አያቃል ፡ ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ ባለው ፡ ሁናቴ ፡ ያከብራቸው ፡ እንጂ ፡

ወያዕርፍ ፡ ባቲ ፡ ነዳያነ ፡ ወአናግደ ከመ ፡
ኢትማስን ፡ ወኢይኅድጋ ፡ ወይረብኅ ፡ ኃጢ
እተ ። ወፈድፋደሰ ፡ ስእመ ፡ ማሰነት ፡ በእንተ ፡
ድንጸዌሁ ፡ ወቅንአቱ ፡ በዝንቱ ፡ ወያሠምሮ ፡
ለሰይጣን ፡ ወይደነጹ ፡ ባቲ ፡ ላዕለ ፡ አግብርተ ፡
እግዚአብሔር ፡ እምእኅው ፡ ነዳያን ፡ ወእለ ፡
ይበጽሑ ፡ ኀበ ፡ አንቀጸ ፡ ምኔት ።

፫፻፸፫ ወይኩን ፡ ዐቃቤ ፡ አንቀጸ ፡ ምኔት ፡ ልምሉመ ፡
ቃል ፡ ስርኑቃነ ፡ ወስቅሩባነ ፡ ወትሑተ ፡ ጥቀ፡
ወተዓጋሤ ፡ እምዕርፈት ፡ ወመርገም ፡ ዘእን
በለ ፡ ተናግሮ ፡ ወዘኢያስተሐቅሮ ፡ ለነዳይ ፡
ወዘይስጠዎ ፡ ፍጡነ ፡ ለዘይጐደጕድ ፡ አንቀጸ ፡
ወዘያከብሮሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ለለአሐዱ ፡ በአ
ምጣነ ፡ ክሂሎቱ ፡ ወሶበ ፡ ሰምዖሙ ፡ ለእለ ፡
ይበውኡ ፡ ወይወፅኡ ፡ እንዘ ፡ ይሔምዮዎ ፡
ለሊቀ ፡ ምኔት ፡ ዘኢያፈጥን ፡ ነጊሮቶ ፡ በዝንቱ ፡
ከመ ፡ ኢይኅዝን ፡ ወኢይትሀወኩ ፡ ሰብእ ፡
ምኔቱ ፡ አላ ፡ ይትዐገሥ ፡ እስከ ፡ ይረክብ ፡
ጊዜ ፡ ዘየኤምር ፡ ቦቱ ፡ ከመ ፡ ሊቀ ፡ ምኔት ፡
ኢይትክዝ ፡ ለእመ ፡ ነገሮ ፡ ወይእተ ፡ ጊዜ ፡ ይን
ግሮ ፡ በሀድአት ፡ ወከሞሳስ ፡ ከመ ፡ ዘይትመከ
ነይ ፡ ሎቱ ፡ ለዘዐረረ ፡ እምድኅረ ፡ አውዕአ ፡
ሎቱ ፡ ቃለ ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ ከመ ፡ ኢይኅዝን ፡
ወኢይትቈጣዕ ፡ ሶበ ፡ ነገሮ ። ወያጠይቆ ፡ ከመ
እለ ፡ መኑ ፡ እሙንቱ ፡ እለ ፡ ያከብርዎ ፡ ወእለ ፡
ያፈቅርዎ ፡ ወእለ ፡ መኑ ፡ እለ ፡ ይጸልእዎ ፡
ወእለ ፡ ያስተሐቅርዎሂ ፡ ወአኮ ፡ በፍኖት ፡ አድ
ልዎ ፡ ሎቱ ፡ አላ ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ይደሉ ፡
ለግብረ ፡ መልእክት ፡ እንተ ፡ ተሠይመ ፡ ላቲ ።
ወይደልዎ ፡ ለሊቀ ፡ ምኔት ፡ ከመ ፡ ኢይክሥት፡
ዘንተ ፡ ዘነግሮ ፡ ዐቃቤ ፡ አንቀጽ ።

፫፻፸፬ ወኢያብሕ ፡ ዐቃቤ ፡ አንቀጽ ፡ ለመኑሂ ፡ እመ
ነኮሳት ፡ ከመ ፡ ይፃእ ፡ እምአንቀጸ ፡ ምኔት ፡
ወኢይኅድግ ፡ መነሂ ፡ ከመ ፡ ይባእ ፡ ኀበ ፡
እኅው ፡ ዘእንበለ ፡ በትእዛዘ ፡ ሊቀ ፡ ምኔት ፡
ወትእምርታቲሁ ፡ ወኢይኅድጎሙ ፡ ይትጋ
ብኡ ፡ ኀቤሁ ፡ በአንቀጸ ፡ ምኔት ፡ ወይንበሩ ፡
በነገረ ፡ መሀድምት ፡ ወስላቅ ፡ ወኢይንሣእ ፡
እምዕዴሆሙ ፡ እምኔሆሙ ፡ ምንተኒ ፡ ወኢያንብር፡
ማኅፀንተ ፡ ሎቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ያእምሩ ፡ እኅው ፡
ወእመ ፡ እንበረ ፡ ኀቤሁ ፡ ፩ዱ ፡ እንግዳ ፡



በገዳሙ ፡ ካስው ፡ ገንዘብ ፡ ጥፋት ፡ ኃፍረት ፡
ባለበት ፡ ምግብ ፡ ይኀብኛቸው ፡ እንዳትጠፋ ፡
ነዳያንን ፡ እንግዶችን ፡ ያሳርፍባት ። እይተዋት፡
ቢተዋትና ፡ ብትጠፋ ፡ ኃጢአትን ፡ ያተርፋል ።
ይልቁንም ፡ ስለ ፡ ንፍገቱና ፡ ስለ ፡ ቅንዐቱ ፡
በዚህ ፡ ብትጠፋ ፡ ሰይጣንን ፡ ደስ ፡ ያሰኘዋል ፡
ከድሆቹ ፡ ከእኃው ፡ ወገን ፡ በእግዚአብሔር ፡
አገልጋዮች ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ገዳሙ ፡ በር ፡ የሚደር
ሱትንም ።

፫፻፸፫ የገዳሙ ፡ በር ፡ ጠባቂ ፡ ለሩቆችም ፡ ለቅርቦ
ችም ፡ ቃለ ፡ ልዝብ ፡ ይሁን ፡ እጅግ ፡ ትሑት ፡
ይሁን ፡ ከመናገር ፡ በቀር ፡ ከስድብና ፡ ከመር
ገም ፡ ታጋሽ ፡ ይሁን ፡ ደሀውን ፡ የማይንቅ ፡
በር ፡ ለሚመታው ፡ ፈጥኖ ፡ የሚከፍትለት ፡
በተቻለው ፡ መጠን ፡ ሁሉንም ፡ ለእያንዳንዳ
ቸው ፡ የሚያከብራቸው ፡ ይሁን ፡ የሚወጡትና፡
የሚገቡት ፡ የገዳሙን ፡ አስተዳዳሪ ፡ ሲያሙት ፡
ቢሰማቸው ፡ በዚህ ፡ እንዳያዝን ፡ የገዳሙም ፡
ሰዎች ፡ እንዳይታወኩ ፡ ፈጥኖ ፡ አይንገረው ።
ቢነግረው ፡ የገዳሙ ፡ አስተዳዳሪ ፡ እንዳያዝን ፡
የሚያመለክትበት ፡ ጊዜ ፡ እስኪያገኝ ፡ ድረስ ፡
ይታገሥ ፡ እንጂ ፡ የገዳሙ ፡ አስተዳዳሪ ፡
ነገር ፡ ከጀመረበት ፡ በኋላ ፡ በሰደበው ፡ ሰው ፡
እያመካኘ ፡ ያንጊዜ ፡ በጸጥታ ፡ በፈገግታ ፡ ይን
ገረው ፡ በነገረው ፡ ጊዜ ፡ እንዳያዝን ፡ እንዳይ
ቆጣ ። የሚያከብሩትና ፡ የሚወዱት ፡ የሚጠ
ሉትና ፡ የሚያስተሐቅሩትም ፡ እነማን ፡ እንደ
ሆኑ ፡ ያስረዳው ። በማድላት ፡ መንገድ ፡ አይደ
ለም ። ይህ ፡ ለተሾመበት ፡ ለአገልግሎት ፡ ሥራ
ስለሚገባ ፡ ነው ፡ እንጂ ። የገዳሙ ፡ አስተዳዳሪ ፡
በር ፡ ጠባቂው ፡ የነገረውን ፡ መሠወር ፡ ይገ
ባዋል ።

፫፻፸፬ በር ፡ ጠባቂው ፡ ከመነኮሳት ፡ ወገን ፡ ከገዳሙ ፡
በር ፡ ይወጣ ፡ ዘንድ ፡ ለማንም ፡ ፈቃድ ፡ አይ
ስጥ ። ያለ ፡ ገዳሙ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ትእዛዝና ፡
ምልክት ፡ በቀር ፡ ወንድሞች ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡
ማንንም ፡ አይተው ። በገዳሙ ፡ በር ፡ ተሰብስ
በው ፡ በተረት ፡ በዋዛ ፡ በፈዛዛ ፡ ይቀመጡ ፡
ዘንድ ፡ አይተዋቸው ። ከእነርሱ ፡ ወገን ፡ ከአን
ዱስ ፡ እንኳ ፡ ምንም ፡ ተቀብሎ ፡ ወንድሞች ፡
ሳያውቁ ፡ አደራ ፡ አያስቀምጥ ። እርሱ ፡ ዘንድ ፡
አንድ ፡ እንግዳ ፡ የገንዘብ ፡ አደራ ፡ ቢያስቀምጥ

ማኅፀንተ ፡ ንዋየ ፡ ዚአሁ ፡ ኢያፍቅሮ ፡ ወኢ
ይበርብር ። ወሶበ ፡ የአምር ፡ ከመ ፡ ሐጸ ፡
ሲሲተ ፡ ምኔት ፡ ለያቅልል ፡ ክበዳ ፡ በቃል ፡
ሠናይ ፡ እንዘ ፡ ይሰድዶሙ ፡ ለአናግድ ፡ በፍ
ቅር ፡ ወበትሕትና ። ወለዘይመጽእ ፡ ውስተ ፡
አንቀጸ ፡ ምኔት ፡ ያስተናሥኦ ፡ ለአስተዋፅኦ ፡
እምዘዚአሁ ፡ ሠናየ ፡ ወኢይትፋቀር ፡ ምስለ ፡
ሰብእ ፡ ዘይጸልእ ፡ ቦቱ ፡ ሊቀ ፡ ምኔት ፡ ላዕ
ሌሆሙ ፡ ወበዘይሬስዮ ፡ እኩየ ፡ ኀቤሆሙ ፡
ወይከውን ፡ በውዴቱ ፡ አምሳለ ፡ ይሁዳ ፡ ዘአስ
ቆሮታዊ ፡ ለመምህሩ ፡ በምክንያተ ፡ እንተ ፡ ቀብ
አቶ ፡ ለእግዚአነ ፡ ዕፍረተ ፡ ወውእቱሰ ፡ በአ
ከየ ፡ ልቡ ፡ አስተርአየ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ወሃቢ ፡
ለነዳያን ።

፫፻፸፮ ሳድስ ፡ በእንተ ፡ ተአዝዞቶሙ ፡ ወተሠርዖ
ቶሙ ። ዘኒቅያ ፡ ወይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡
ጉባኤ ፡ አኃው ፡ አዝሳፍያነ ፡ ጾም ፡ ወጸሎት ፡
ወእንብቦተ ፡ መጻሕፍት ፡ ቅዱሳት ፡ በከመ ፡
አዘዞሙ ፡ ሊቀ ፡ ምኔት ፡ ወይትለአኩ ፡ በእብሬ
ቶሙ ፡ ለለስሙን ፡ በውሳጤ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ
ያን ፡ ወአፍአሃ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ መልእክት ፡
ክህነታዊት ፡ ወሥጋዊት ፡ ወሶበ ፡ በጽሐ ፡
ኀቤሆሙ ፡ ፩ዱሂ ፡ መነኰስ ፡ እንግዳ ፡ ያዕብ
ይዎ ፡ ወያክብርዎ ፡ ወያንብርዎ ፡ ምስሌሆሙ ፡
ውስተ ፡ ማእድ ፡ ወያዕርፍዎ ። ወሕዝባውያንሰ
ይብልዑ ፡ በባሕቲቶሙ ፡ በገቦ ። ወቦ ፡ እምኔ
ሆሙ ፡ ዘያነብሮ ፡ ሊቀ ፡ ምኔት ፡ ምስሌሁ ፡
በማእዱ ፡ በእንተ ፡ ግብር ፡ ዘይደሉ ፡ ለበቍ
ዔተ ፡ ምኔት ።

፫፻፸፯ ዘ፯ወ፩ዱ ፡ ወከመ ፡ ይንበሩ ፡ በምግባር ፡
ሠናይ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ወምስለ ፡ ኵሉ ፡
ሰብእ ፡ ወኢይሑሩ ፡ ውስተ ፡ ምሥያጣት ፡ ወፍ
ናዋት ፡ ሑረተ ፡ ዘአልቦ ፡ ኀፍረት ፡ ወዘእን
በለ ፡ ህድአት ፡ ወኢይትናበቡ ፡ በበይናቲሆሙ ፡
በነገረ ፡ ሰላቅ ፡ ወኀፍረት ፡ እንዘ ፡ ይስሕቁ ፡
ወይዛውዑ ፡ አላ ፡ ይፀመዱ ፡ ለአርምሞ ፡ ወለ
ህድአት ፡ ወፈድፋደሰ ፡ በኀበ ፡ ዓላውያነ ፡
ሃይማኖት ።

፫፻፸፰ ወይሠርገዉ ፡ በኵሉ ፡ ሠርጕ ፡ መንፈሳዊ ፡ ወኢ
የኀትጋወርዎን ፡ ለአንስት ፡ ወኢይብልዑ ፡ ሥጋ
ው... ፡ ምኔታቲሆሙ ፡ ወኢ ፡ ውስተ ፡ ካል
እ... ። ወኢይሠርገዉ ፡ ወኢይትቀብኡ ፡ ዕፍ
ረተ ። ወይቅንቱ ፡ ሐቌሆሙ ፡ በቅናት ፡ እም



አይፍታ ፡ አይበርብርም ። የገዳሙ ፡ ምግብ ፡
እንዳለቀ ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ እንግዶቹን ፡ በፍቅርና ፡
በትሕትና ፡ እየሸኘ ፡ በበጎ ፡ ቃል ፡ ችግሯን ፡
ያቃልል ። ወደገዳሙ ፡ በር ፡ የሚመጣውን ፡
ሰው ፡ ካለው ፡ በጎ ፡ አስተዋፅኦ ፡ ያወጣጣ ፡
ዘንድ ፡ ያነሣሣው ፤ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ የገዳሙ ፡
አስተዳዳሪ ፡ ከሚጠላው ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ አይፋ
ቀር ፡ በእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ክፉ ፡ በሚያደርገው ፡
ገንዘብ ፡ በነገር ፡ ሥራው ፡ ጌታችን ፡ ሽቱ ፡ በቀ
ባችው ፡ ሴት ፡ ምክንያት ፡ መምህሩን ፡ የካ
ደው ፡ የይሁዳ ፡ አምሳል ፡ ይሆናል ፡ እርሱ ፡
ግን ፡ በልቡ ፡ ክፋት ፡ ለድሆች ፡ እንደሚሰጥ ፡
አስረዳ ።

፫፻፸፮ ስድስተኛ ፡ ስለመታዘዛቸውና ፡ ስለመስማማታ
ቸው ፡ ይናገራል ። ኒቅያ ፡ የተሰበሰቡ ፡ ወንድ
ሞች ፡ ጾምና ፡ ጸሎትን ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት
ንም ፡ ማንበብ ፡ የሚያዘወትሩ ፡ ሊሆኑ ፡ ይገ
ባል ። የገዳሙ ፡ አስተዳዳሪ ፡ እንዳዘዛቸው ፡ በሥ
ጋዊና ፡ በክህነታዊ ፡ አገልግሎት ፡ በቤተ ፡ ክር
ስቲያን ፡ ውጭና ፡ ውስጥ ፡ በየሳምንቱ ፡ በአየ
ስሞናቸው ፡ ያገልግሉ ። አንድ ፡ እንግዳ ፡ መነ
ኵሴ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ፈጽመው ፡
ያከብሩት ፡ በማዕድ ፡ ጊዜ ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡
ያስቀምጡት ፡ ያሳርፉትም ። ሕዝባውያን ፡
ግን ፡ ብቻቸውን ፡ በጎን ፡ ይብሉ ፡ ለገዳሙ ፡
ጥቅም ፡ ስለሚገባ ፡ ሥራ ፡ ከነርሱ ፡ ወገን ፡ አበ
ምኔቱ ፡ በማዕድ ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ የሚያስቀም
ጠው ፡ አለ ።

፫፻፸፯ ፲፯ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ከሰውም ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡
በበጎ ፡ ሥራ ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ወደገብያና ፡
ወደመንገድ ፡ ያለጸጥታ ፡ ኀፍረት ፡ የሌለው ፡
አካሄድ ፡ አይሂዱ ። እርስ ፡ በርሳቸው ፡ እየሣቁ ፡
እየተጫወቱ ፡ በሚያሳፍርና ፡ በስሐቅ ፡ ነገር ፡
አይነጋገሩ ፡ ለብሕትውናና ፡ ለጸጥታ ፡ ይጸ
መዱ ፡ እንጂ ፡ ይልቁንም ፡ ሃይማኖት ፡ በሌላ
ቸው ፡ ዘንድ ።

፫፻፸፰ በመንፈሳዊ ፡ ጌጥ ፡ ሁሉ ፡ ያጊጡ ፡ ሴቶቹንም ፡
አይጐራበቷቸው ፡ በገዳሞቻቸውና ፡ በሌላይቱ ፡
ውስጥ ፡ ሥጋ ፡ አይብሉ ፡ አያጊጡ ፡ ሽቱ ፡ አይ
ቀቡ ፡ ከደንሳ ፡ ማስ ፡ ወገን ፡ በዝናር ፡ ወገባቸ
ውን ፡ ይታጠቁ ፡ ልብሳቸውም ፡ ከደንሳ ፡

አምአስት ፡ ገዚፋን ፡ ወይኩን ፡ ልብሶሙ ፡ አም ፀምር ፡ ግዙፍ ፡ ልብስ ፡ መናንያን ።

፫፻፸፰ ወከማሁ ፡ አርአያሆሙ ፡ በኵሉ ፡ ግብሮሙ ፡ ይኩን ፡ ካልአ  አምአርአያ ፡ ሕዝባውያን ፡ ወይ ርኅቁ ፡ እምሥርጉ ፡ ሕዝባውያን ፡ ወልማዳቲ ሆሙ ፡ ከመ ፡ አበው ፡ አለ ፡ ነሣአነ ፡ አምኔ ሆሙ ፡ ግብረ ፡ ትሩፋት ፡ ወሠናያት ፡ ወኮኑ ፡ መነኩሳተ ፡ በጽድቅ ፡ ወየሐልዩ ፡ በነፍሶሙ ፡ ከመ ፡ ውእቶሙ ፡ ምዉታን ።

፫፻፸፱ ምጣኔ ፡ መብልዕኒ ፡ ወስቴ ፡ ወአልባስ ፡ ለእመ ፡ ኮኑ ፡ ፈድፋደ ፡ መስተገብራነ ፡ ምድር ፡ ላስ ብአ ፡ ምኔት ፡ ይደልዎሙ ፡ ይብልዑ ፡ ፪ተ ፡ ጊዜ ፡ በ፩ዱ ፡ ዕለት ፡ ቀዳሚ ፡ በ፮ቱ ፡ ሰዓት ፡ ወካልአ ፡ በተፍጻሜተ ፡ መዓልት ። ወለእመስ ፡ ኢኮኑ ፡ መስተገብራነ ፡ ምድር ፡ የአክሎሙ ፡ ፩ደ ፡ ጊዜ ፡ አመኒ ፡ በ፱ቱ ፡ ሰዓት ፡ አው ፡ በፍ ጻሜ ፡ መዓልት ። ወይኑሙ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ኅበ ፡ በዓቶሙ ።

፫፻፹ ወርእስ ፡ ምኔትስ ፡ ወድዉያን ፡ አምአኃው ፡ እመ ፡ ፈቀዱ ፡ ከመ ፡ ይኑሙ ፡ ላዕለ ፡ ዓራት ፡ ይደልዎሙ ፡ በእንተ ፡ ክብሮሙ ፡ ወደዌሆሙ ፡ ወኢያውዕኡ ፡ አልባሲሆሙ ፡ አምኔሆሙ ። ወሶበ ፡ ፈቀዱ ፡ ነዊመ ፡ ኢይደሉ ፡ ሎሙ ፡ ከመ ፡ ይፍትሑ ፡ ቅናቶሙ ፡ ወኢይኑሙ ፡ ፪ቱ ፡ ላዕለ ፡ ፩ዱ ፡ ዓራት ፡ ወኢይትላጸቁ ፡ በበይና ቲሆሙ ። አላ ፡ ይኩኑ ፡ ድልዋነ ፡ ለጸሎት ፡ ወለ ትጋህ ፡ በከመ ፡ ይዴለዉ ፡ ሠራዊት ፡ ለዕለተ ፡ ጸብእ ፡ ወሰዓተ ፡ ቀትል ።

፫፻፹፩ ወለእመ ፡ በዝኀ ፡ ጸማ ፡ ወቅኔ ፡ ላዕለ ፡ ድኩ ማን ፡ ያዕርፍዎሙ ፡ ወይኅድግዎሙ ፡ ኑኀ ፡ መዋዕል ፡ እስከ ፡ ይፌጽሙ ፡ ጸሎተ ፡ በባሕቲ ቶሙ ። ወጥዑያንሰ ፡ ይትገበሩ ፡ በበዕብሬቶሙ ፡ ወየሀብዎሙ ፡ አልባስ ፡ እምድኅረ ፡ በዓለ ፡ መስቀል ።

፫፻፹፪ ወእመ ፡ በጽሐ ፡ ክረምት ፡ ይጽሐፉ ፡ አስማቲ ሆሙ ፡ በእንተ ፡ እልባሲሆሙ ፡ ወዓራዛቲሆሙ ፡ እስከ ፡ ሐጋይ ። ወያንብርዋ ፡ በመዛግብተ ፡ ምኔት ፡ እስከ ፡ የአምሩ ፡ ነሢአታ ፡ በፍጻሜ ፡ ክረምት ። ወከማሁ ፡ ይግበሩ ፡ በልብሶሙ ፡ ዘክረምት ፡ ጊዜ ፡ ብጽሐተ ፡ ሐጋይ ። ወይጊሡ ፡ በሐጋይ ፡ ኀበ ፡ ተግባሮሙ ። ወበጊዜ ፡ ሐሩር ፡ ይንበሩ ፡ እስከ ፡ ጊዜ ፡ ጸሎት ፡ ዘመንፈቀ ፡ መዓልት ። ወእምድኅረ ፡ ጸለዩ ፡ ይብልዑ ፡



ግምጃ ፡ ወገን ፡ የመናንያን ፡ ልብስ ፡ ይሁን ።

፫፻፸፰ እንደዚሁ ፡ በሥራቸው ፡ ሁሉ ፡ መልካቸው ፡ ከሕዝባውያን ፡ መልክ ፡ ልዩ ፡ ይሁን ። ከሕዝባ ውያን ፡ ጌጥ ፡ ከልማዳቸውም ፡ ይራቁ ፡ የትሩ ፋትና ፡ የበጎ ፡ ሥራን ፡ ከነርሱ ፡ እንደ ፡ ተቀበ ልናቸው ፡ እንደ ፡ አባቶች ፡ በእውነትም ፡ መነ ኩሳት ፡ እንደሆኑ ፡ እነሱ ፡ ምዉታን ፡ እንደሆኑ በልባቸው ፡ ያስቡ ።

፫፻፸፱ የምግብ ፡ የመጠጥ ፡ የልብስ ፡ ልክ ፡ እንዲህ ፡ ይሁን ። ለማኅበሩ ፡ ፈጽሞ ፡ የምድር ፡ አራሾች ፡ ቢሆኑ ፡ በአንድ ፡ ቀን ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ መብላት ፡ ይገባቸዋል ፡ መጀመሪያ ፡ በስድስት ፡ ሰዓት ፡ ፪ኛ ፡ በአሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ገበሬዎች ፡ ባይ ሆኑ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይበቃቸዋል ፡ በ፱ ሰዓት ፡ ወይም ፡ በ፲፪ ፡ ሰዓትም ፡ ቢሆን ፡ በቤ ታቸው ፡ ከምድር ፡ ይተኙ ።

፫፻፹ አበ ፡ ምኔቱና ፡ ከወንድሞች ፡ ወገን ፡ በሽተ ኞች ፡ የሆኑት ፡ ግን ፡ በአልጋ ፡ ሊተኙ ፡ ቢወዱ፡ ስለክብራቸውና ፡ ስለደዌያቸው ፡ ይገባቸዋል ። ልብሳቸውንም ፡ ከሰውነታቸው ፡ አያውልቁ ፡ ሊተኙ ፡ ቢወዱ ፡ ቅናታቸውን ፡ ሊፈቱ ፡ አይገ ባም ፡ ሁለቱ ፡ በአንድ ፡ አልጋ ፡ አይተኙ ፡ እርስ በእርሳቸው ፡ አይተቃቀፉ ፡ ለጸሎት ፡ ለመስ ገድ ፡ የተዘጋጁ ፡ ይሁኑ ፡ እንጂ ፡ ወታደሮች ፡ ለጠብ ፡ ቀንና ፡ ለውጊያ ፡ ሰዓት ፡ እንደሚዘ ጋጁ ።

፫፻፹፩ ድካም ፡ አገልግሎት ፡ በደካሞቹ ፡ ላይ ፡ ቢበዛ ፡ ያሳርፏቸው ። በብቻቸው ፡ ጸሎቱን ፡ እስኪፈ ጽሙ ፡ ድረስ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ይተዋቸው ፡ ጤነ ኞች ፡ ግን ፡ በተራቸው ፡ ይሥሩ ፡ ከመስቀል ፡ በዓል ፡ በኋላ ፡ ልብሳቸውን ፡ ይስጧቸው ።

፫፻፹፪ ክረምት ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ በልብሳቸውና ፡ በቀሚ ሳቸው ፡ ላይ ፡ ስማቸውን ፡ ጽፈው ፡ እስከ ፡ በጋ፡ ድረስ ፡ በገዳሙ ፡ ዕቃ ፡ ቤት ፡ ያስቀምጧት ፡ ክረምቱ ፡ እንደወጣ ፡ አውቀው ፡ እስኪያነሷት፡ ድረስ ፡ በጋም ፡ በደረስ ፡ ጊዜ ፡ በክረምት ፡ ልብ ሳቸው ፡ ላይ ፡ እንደዚሁ ፡ ያድርጉ ። በማለዳ ፡ ወደ ፡ ሥራቸው ፡ ይገሥግሡ ፡ በሐሩር ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ ቀኑ ፡ የቀትር ፡ ጸሎት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ይቀ መጡ ፡ ከጸለዩ ፡ በኋላ ፡ ይብሉ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡

ወእምዝ ፡ ያዕርፉ ፡ እስከ ፡ የኀልፍ ፡ ዋዕይ ። ወእምድኅረ ፡ ቊረ ፡ መዓልት ፡ ይትመየጡ ፡ ኀበ ፡ ተግባሮሙ ፡ እስከ ፡ ምሴት ፡ ወእምድኅረ ፡ ጸለዩ ፡ ይደረሩ ።

፫፻፹፫ ወይክፍልዎ ፡ ለመዓልት ፡ ኀበ ፡ ፫ቱ ፡ መክፈልት ፡ ፩ ፡ ክፍል ፡ ለጸሎት ፡ ወለአንብቦ ፡ ወካልኡ ፡ ክፍል ፡ ለመብልዕ ፡ ወሣልሱ ፡ ክፍል ፡ ለተገብሮ ፡ ወያዕርፉ ፡ በማእከለ ፡ እሉ ። በእንተ ፡ ሰቱስ ፡ ይስተዩ ፡ በእምጣነ ፡ ይፈቅድ ፡ ሥጋ ፡ ለበቍዔት ፡ በከመ ፡ አዘዘ ፡ ጳውሎስ ፡ ለረድኡ ።

፫፻፹፬ ዘኒቅያ ፡ ወለእመስኬ ፡ ሕዝባውያን ፡ ሶበ ፡ ነግዱ ፡ በንዋይ ፡ ይከውኖሙ ፡ ነውረ ፡ ሚመጠን ፡ ይከውኖሙ ፡ ነውረ ፡ ለመነኮሳት ፡ ሶበ ፡ ነግዱ ።

፫፻፹፭ በሰ ፡ ወኢይደልዎ ፡ ለመናኒ ፡ ከመ ፡ ይፍቱ ፡ ሢመተ ፡ ክህነት ፡ ወኢ ፡ ሊቀ ፡ ምኔት ። እስመ ፡ ፍቅረ ፡ ሢመት ፡ ደዌ ፡ ሰይጣናዊ ፡ ውእቱ ፡ ወዘወድቀ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ሕማም ፡ ይከውን ፡ ቀናኤ ፡ ላዕለ ፡ እለ ፡ ይደልዎሙ ፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ ካህናተ ፡ ወሥዩማነ ፡ ወይቀጽብ ፡ ሰብአ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ወያስተናሥእ ፡ ወየኀሥሥ ፡ ሞቶሙ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ውእቱ ፡ በመዓርጊሆሙ ፡ ወሶበ ፡ ኮነ ፡ ሎቱ ፡ ኢንኢድ ፡ ይከውን ፡ ማእከሌሁ ፡ ወማእከሌሆሙ ፡ ሁከት ። ይረንቅኬ ፡ እምዝንቱ ፡ ፍትወት ፡ እኩይ ። ወሶበ ፡ ሠምረ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዘይቀውም ፡ ለሢመት ፡ ውእቱ ፡ ባሕቲቱ ፡ የአምር ፡ ዘይሠይሞ ፡ ወይደልዎ ፡ ለዕሙድ ፡ ከመ ፡ ይትፈለጥ ፡ በኮሉ ፡ ልቡ ፡ እምአበዊሁ ፡ ወእዝማዲሁ ፡ ወሰብአ ፡ ሕዝባውያን ፡ ከመ ፡ ተፈልጦተ ፡ ምዉት ፡ እምሕያዋን ።

፫፻፹፮ ወለእመ ፡ ቦኡ ፡ ኀበ ፡ ምንኮስና ፡ እሚሃ ፡ ይትመየጡ ፡ ኀበ ፡ ተዘምዶቱ ፡ እላ ፡ ኢይኩን ፡ ሎሙ ፡ ላዕሌሁ ፡ መዓርግ ፡ እበውና ፡ ዳእሙ ፡ መዓርግ ፡ እኀውና ፡ እስመ ፡ ለኮሎሙ ፡ አቡሆሙ ፡ በጽድቅ ፡ ቀዳማዊ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አበ ፡ ኮሉ ፡ ወዳግማዊኒ ፡ እምድኅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ አብ ፡ መንፈሳዊ ፡ ሊቅ ፡ ዘላዕለ ፡ ዛቲ ፡ ትሩፋት ። ወለአዝማዲሁ ፡ ቅሩባን ፡ በሥጋ ፡ ለይኅሥሥ ፡ ሎሙ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ አምልኮ ፡ ንጽሕተ ፡ በዘ፣የስ ተሐምም ፡ ሎሙ ፡ እው ፡ ይሕትት ፡ በእንተ ፡

ዋዕዩ ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ ይረፉ ። ቀኑ ፡ ከቀዘ ቀዘ ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ ምሽቱ ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ ሥራ ቸው ፡ ይመለሱ ፡ ከጸለዩም ፡ በኋላ ፡ ይመገቡ ።

፫፻፹፫ ቀኑን ፡ ከሦስት ፡ ይከፈሉት ። አንዱን ፡ ክፍል ፡ ለጸሎት ፡ ለማንበቢያ ፡ ሁለተኛውን ፡ ክፍል ፡ ለምግብ ፡ ሦስተኛውን ፡ ክፍል ፡ ለሥራ ፡ በእነ ዚሁ ፡ መካከልም ፡ ይረፉ ። ስለመጠጥ ፡ ግን ፡ ጳውሎስ ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩን ፡ እንዳዘዘ ፡ ሥጋ ፡ ለጥቅም ፡ በሚያሻው ፡ መጠን ፡ ይጠጡ ።

፫፻፹፬ ኒቅያ ፡ ሕዝባውያን ፡ በገንዘብ ፡ ቢነግዱ ፡ የሚያ ሰነውራቸው ፡ ከሆነ ፡ መነኰሳትማ ፡ ቢነግዱ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ያሰነውራቸው ፡ ይሆን ?

፫፻፹፭ በሰ ፡ መናኝ ፡ የክህነት ፡ የአበ ፡ ምኔትነት ፡ ሹመት ፡ መውደድ ፡ አይገባውም ፡ የሹመት ፡ ፍቅር ፡ ሰይጣናዊ ፡ በሽታ ፡ ነውና ፡ በዚህ ፡ በሽታ ፡ ላይ ፡ የወደቀ ፡ ሰው ፡ ካህናትና ፡ ሹማምት ፡ ሊሆኑ ፡ በሚገባቸው ፡ ላይ ፡ ቀና ተኛ ፡ ይሆናል ። ሰው ፡ ጠቅሶ ፡ ያነጣጣባቸ ዋል ። በእነርሱ ፡ ሹመት ፡ ይተካ ፡ ዘንድ ፡ ሞታቸውን ፡ ይወዳል ። ሹመቱ ፡ ባልሆነለት ፡ ጊዜ ፡ በርሱና ፡ በእነርሱ ፡ መካከል ፡ ችግር ፡ ይፈጠራል ፡ ከዚህ ፡ መጥፎ ፡ ፈቃድ ፡ ይራቅ ፡ እንጂ ። ለሹመት ፡ በሚበቃ ፡ ገንዘብ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ከወደደ ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ የሚሾመውን ፡ ያውቃል ። መናኝ ፡ በፍጹም ፡ ልቡ ፡ ከወላጆቹ ፡ ከዘመዶቹ ፡ ከሕዝባውያን ፡ ወገን ፡ ከወገኖቹ ፡ መለየት ፡ ይገባዋል ፡ ሙት ፡ ከደኅንኞቹ ፡ እንደ ሚለይ ።

፫፻፹፮ ቢመነኵሱ ፡ የንጊዜ ፡ ወደ ፡ ዘምድና ፡ ይመለሱ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የአባትነት ፡ መዓርግ ፡ አይኑራ ቸው ፡ የወንድምነት ፡ መዓርግ ፡ ይኑራቸው ፡ እንጂ ። መጀመሪያው ፡ በእውነት ፡ የሁሉም ፡ አባታቸው ፡ የሁሉ ፡ አባት ፡ እግዚአብሔር ፡ ነውና ። ሁለተኛውም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በታች በዚህች ፡ ትሩፋት ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ መንፈሳዊው ፡ አስተዳዳሪ ፡ ነው ። በሥጋ ፡ ቅርቦች ፡ ለሆኑት ፡ ዘመዶቹ ፡ ግን ፡ በሚያስብላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ንጹሕ ፡ አምልኮትን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ይለምንላቸው ፡ ወይም ፡ ሥራቸውን ፡ ይመር

ምግባራቲሆሙ ፡ ወእይኅድጎሙ ፡ በዝኩ ፡ ከመ ፡ ኢያብእ ፡ መስሕት ፡ ውስተ ፡ ልቦሙ ፡ ወውስተ ፡ ሕሊናሆሙ ፡ እኪተ ፡ ወሐልዮ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ እንተ ፡ ርኅቅነ ፡ እምኔሁ ፡ ወንከውን ፡ ከመ ፡ ጣዖታት ፡ ዘላዕሌሆሙ ፡ አር አያ ፡ ምንኵስና ፡ ወእልቦ ፡ ውስቴቶሙ ፡ ነፍስ ፡ ዘትገብር ፡ ትሩፋተ ፡ ምንኵስና ።

፫፻፹፯ ወእግዚእነሂ ፡ ኢያብሖ ፡ ለዘፈቀደ ፡ ይኩን ፡ ሎቱ ፡ ረድአ ፡ ከመ ፡ ይሥራዕ ፡ ሰብአ ፡ ቤቱ ፡ ወከመ ፡ ይቅብሮ ፡ ለአቡሁ ፡ ወኢከመ ፡ ይነ ጽር ፡ ኀበ ፡ ድኅሬሁ ። ለእለሰ ፡ ይበውኡ ፡ ውስተ ፡ ዛቲ ፡ ሱታፌ ፡ ኢይከውን ፡ ለዕዱሂ ፡ እምኔሆሙ ፡ ግብር ፡ ዘዚአሁ ፡ ወኢለርእሱ ፡ እንተ ፡ መጠም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወኵሉ ፡ ግብር ፡ ዘሎሙ ፡ ነዋ ፡ ኮነ ፡ ሕሩመ ፡ ለእግዚአ ብሔር ፡ ወእልቦቱ ፡ ለዕዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ሥል ጣን ፡ ላዕለ ፡ ምንትኒ ፡ ይግበር ፡ አምኔሁ ፡ ግብረ ፡ ለዓለማውያን ፡ ወኢለቅሩባኒሁ ፡ ሥጋውያን ፡ ወኢለርእሱ ፡ አላ ፡ ለእኀዊሁ ፡ መነኮሳት ፡ ዘኮነ ፡ ዕዱ ፡ ፆታ ። ወለእክልቲኒ ፡ አልቦሙ ፡ ሥልጣን ፡ ላዕለ ፡ ርእሶሙ ፡ ከመ ፡ ይትፈለጡ ፡ እማእሰረ ፡ ተአኅዎት ፡ መንፈሳ ዊት ፡ በከመ ፡ ኢይትከሀል ፡ ተፈልጦተ ፡ ተላ ጽቆተ ፡ አባል ፡ ጠባይዓዊ ፡ ወተፈልጦተ ፡ ተዋ ስቦ ፡ ዘእንበለ ፡ በሞት ።

፫፻፹፰ ወለእመቦ ፡ ዘይብል ፡ እስመ ፡ አኀው ፡ እኩ ያን ፡ እሙንቱ ፡ ንብሎ ፡ እኮ ፡ ኵሎሙ ፡ ወሐዋ ርያትኒ ፡ ኢተፈልጡ ፡ እምተጋብኦቶሙ ፡ በእ ንተ ፡ እከዩ ፡ ለይሁዳ ፡ ወኢክሀለ ፡ ጥውየቱ ፡ ከመ ፡ ይማዕ ፡ ርትዓተ ፡ ልቡ ፡ ለዕዱ ፡ እምኔ ሆሙ ፡ ከመ ፡ ኢይፈጽም ፡ ተእዝዞቶ ፡ ለክርስ ቶስ ። ወተፀምዶስ ፡ እማናዊ ፡ ከመ ፡ ተእኅዝ ፡ ቅድመ ፡ ንጻሬከ ፡ ወምስማዐከ ፡ ከመ ፡ ኢያ ብእ ፡ ኀበ ፡ ነፍስከ ፡ ዘያማስና ፡ ወእምዝ ፡ ሐል ዮተከ ፡ ወልሳነከ ፡ ከመ ፡ ኢይፃእ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘያረኵሳ ።

፫፻፹፱ ወይደልወነ ፡ ከመ ፡ ንኅረይ ፡ እመባልዕት ፡ ወእልባሳት ፡ ዘየአክል ፡ ወይሤኒ ፡ ወንዘክር ፡ ቃለ ፡ ዘይቤ ፡ "እነ ፡ እመልእ ፡ ሰማየ ፡ ወም ድረ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአነ ፡ አምላክ ፡ ቅሩብ ፡ ወዘኢኮንኩ ፡ ርኁቀ" ። ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ "ኀበ ፡ ሀለዉ ፡ ፪ቱ ፡ ወ፫ቱ ፡ በስምየ ፡ ጉቡአን ፡



ምር ። ወደልባቸው ፡ ሰሕተት ፡ ወደ ፡ ሕሊና ቸው ፡ ክፋት ፡ እኛ ፡ ከርሱ ፡ የራቅነው ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ አሳብም ፡ እንዳይገባ ፡ አይተዋቸው ። የምንኵሰና ፡ መልክ ፡ እንዳላቸው ፡ ጣዖታት ፡ እንሆናለን ፡ የምንኵስናን ፡ ትሩፋት ፡ የምት ሠራ ፡ ነፍስ ፡ የሌቻቸውም ።

፫፻፹፯ ጌታችንም ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ሊሆነው ፡ የወደ ደውን ፡ ቤተ ፡ ሰቡን ፡ ይሰናበት ፡ ዘንድ ፡ አባ ቱንም ፡ ይቀብር ፡ ዘንድ ፡ ወደኋላውም ፡ ይመ ለስ ፡ ዘንድ ፡ አላሰናበተውም ። (ማቴ ፡ ፰ ፡ ፳፩-፳፪) ወደዚህች ፡ አንድነት ፡ ከሚገቡ ፡ ሰዎች ፡ አንዱስ ፡ እንኳ ፡ የተለየ ፡ ሥራ ፡ መሥሪት ፡ አይገባውም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሰጠውን ፡ የራሱንም ፡ ቢሆን ፡ ሥራቸው ፡ ሁሉ ፡ እነሆ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተለየ ፡ ሆነ ፡ ከእነርሱ ፡ ወገን ፡ ለአንዱ ፡ ከራሱ ፡ አንቅቶ ፡ ለዓለማው ያን ፡ ለሥጋውያን ፡ ዘመዶቹ ፡ ለራሱም ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣን ፡ የለውም ፡ ለወንድ ሞቹ ፡ መነኰሳት ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ወገ ን ፡ የሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ። ከመንፈሳዊ ፡ ወንድም አንድነት ፡ ይለዩ ፡ ዘንድ ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ ለእነዚህም ፡ ሥልጣን ፡ የላቸውም ፡ የተፈጥሮ ፡ አካል ፡ አንድነትን ፡ መለየት ፡ እንደማይቻል ፡ ከሞት ፡ በቀር ፡ ጋብቻንም ፡ መለየት ፡ እንደማ ይቻል ።

፫፻፹፰ ወንድሞች ፡ እኮ ፡ ክፉዎች ፡ ናቸው ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ መላው ፡ አይደሉም ፡ እንለዋለን ፡ ሐዋርያትም ፡ ስለይሁዳ ፡ ክፋት ፡ ከመሰብሰብ ፡ አልተለዩም ፡ ጥመቱ ፡ ከእነርሱ ፡ ወገን ፡ የአን ዱን ፡ ልብ ፡ ቅንነት ፡ ሊያቸንፈው ፡ አልቻለም ፡ የክርስቶስን ፡ ትእዛዝ ፡ እንዳይፈጽም ፡ እውነ ተኛ ፡ ምናኔስ ፡ ከማየት ፡ ከመስማት ፡ አስቀ ድሞ ፡ መከልከል ፡ ነው ፡ የሚጎዳህን ፡ ወደ ሰውነትህ ፡ እንዳያገቡ ፡ ከነዚህም ፡ ቀጥሎ ፡ እንደበትህንና ፡ ሐሳብህን ፡ መወሰን ፡ ነው ፡ ከእነርሱም ፡ የሚያረክስ ፡ እንዳይወጣ ።

፫፻፹፱ ከምግብና ፡ ከልብስ ፡ ወገን ፡ የሚበቃውንና ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መውሰድ ፡ ይገባናል ፡ «እግዚአብሔር ፡ እኔ ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ እመላለሁ ፡ እኔ ሩቅ ያይደለሁ ፡ ቅርብ ፡ አም ላክ ፡ ነኝ ።» (ኤር ፡ ፳፫ ፡ ፳፫-፳፬) ። ያለውን ፡ ቃል ፡ እናስብ ፡ ዳግመኛም ፡ «ሁለቱ ፡ ሦስቱ ፡

እነ ፡ እሄሉ ፡ ሀየ ፡ ማእከሎሆሙ” ፡ ወይደል ወነ ፡ ከመ ፡ ንፈጽም ፡ ኵሎ ፡ ግብረ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሬእየነ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ግብር ፡ ወከመዝ ፡ ትኩን ፡ ውስቴትነ ፡ ፍርሃቱ ፡ ወንፈ ጽም ፡ ፈቃዳቲሁ ፡ ወኢንግበር ፡ ትእዛዞ ፡ ለአ ሥምሮተ ፡ ሰብእ ።

፫፻፶ ወሀልዎተ ፡ ማኅበርሰ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ረባኅ ፡ ውእቱ ፡ በብዙኅ ፡ ፆታ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆ ፡ እስመ ፡ ለሰብእ ፡ ኢይትከሀሎ ፡ ይብቋዕ ፡ ባሕቲቱ ፡ ለመፍቅደ ፡ ሥጋሁ ፡ ወካዕበ ፡ እስመ ፡ ፍቅር ፡ መሚሐዊት ፡ ወትእዛዝ ፡ ሐዋርያዊት ፡ ትኤዝዝ ከመ ፡ ይኩን ፡ ኵሉ ፡ እምኔነ ፡ ዘየኀሥሥ ፡ ዘይበቊዖ ፡ ለባሕቲቱ ፡ እላ ፡ በዘይረብኖ ፡ ለእ ብያጺሁ ።

፫፻፶፩ ወካዕበ ፡ እስመ ፡ ባሕታዊ ፡ ኢየአምር ፡ ሕጸጸ ፡ ርእሱ ፡ ወሶበሂ ፡ ተገበረ ፡ ለፈጽሞ ፡ አሐቲ ፡ ትእዛዝ ፡ ታመሥጦ ፡ ካልእት ፡ ምሳሌ ። ወሶ በኒ ፡ ሐወጸ ፡ ድዉየ ፡ ያመሥጦ ፡ ተወክፎተ ፡ እንግዳ ። ወእፎኬ ፡ ይትከሀሎ ፡ ከመ ፡ ይትወ ከፍ ፡ ሀብታተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወይእቲሰ ፡ ፈድፋደ ፡ ኢትትወሀቦ ፡ ዘእንበለ ፡ ከመ ፡ ይት ለአክ ፡ ባቲ ፡ ለካልኡ ። ወሶበኒ ፡ ነሥአ ፡ ትነ ብር ፡ ኅብእተ ፡ በርእሱ ፡ ወኢይረብኖ ፡ ባቲ ፡ ካልኡ ፡ ወውእቱኒ ፡ ኢይረብኖ ፡ እምካልኡ ። በውስተ ፡ ጉባኤሰ ፡ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ለለ፩ዱ ፡ ይበቊዖ ፡ ሀብቱ ፡ ዚአሁ ፡ ወሀብቱ ፡ ካልኡ ።

፫፻፶፪ ወባሕታዊሰ ፡ ለእመ ፡ ኖመ ፡ ኢይረክብ ፡ ዘያነ ቅሖ ፡ ወኢይረክብ ፡ ዘይረክቦ ፡ በጉባኤ ፡ እም ቃለ ፡ ተማኅጽ ፡ በእንተ ፡ እጽንዖ ፡ ወተውሳክ ፡ በወድሶት ፡ እኅው ፡ ወይትሔዘብ ፡ ከመ ፡ ው እቱ ፡ በጽሐ ፡ ኀበ ፡ ፍጻሜ ፡ ትሩፋት ፡ ወእ መኒ ፡ ኮነ ፡ ሕጹጸ ፡ ውእቱ ፡ ወኢይትከሀሎ ፡ ከመ ፡ ይፈጽም ፡ ግብረ ፡ ትሕትና ፡ ወኢተራ ኅርኖ ፡ በእንተ ፡ ዘኢረከበ ፡ ዘይቴሕት ፡ ሎቱ ፡ እው ፡ ይትራኅራኅ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወእፎ ፡ ይክሙን ፡ ነዊኀ ፡ መንፈስ ፡ እንዘ ፡ አልቦ ፡ ኀቤሁ ፡ ብእሲ ፡ ዘይትቃረን ፡ ሥምረቶ ፡ ዚአሁ ።

፫፻፶፫ ወእመኒ ፡ ይቤ ፡ እስመ ፡ መጽሐፍ ፡ ትበቊዖ ፡ ከመ ፡ ትምሀሮ ፡ አቅሞተ ፡ ትሩፋት ፡ ለያእ



በስሜ ፡ ተሰብስበው ፡ ካሉበት ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ ከዚያ ፡ በመካከላቸው ፡ እኖራለሁ ።» አለ ፡ (ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፳) በሥራው ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ እንደሚያየን ፡ አውቀን ፡ ሥራውን ፡ ሁሉ ፡ መፈጸም ፡ ይገባናል ። ርሱን ፡ መፍራታ ችን ፡ በልባችን ፡ እንደዚህ ፡ ትሁን ፤ ፈቃዱ ንም ፡ እንፈጽም ፤ ትእዛዙንም ፡ ሰውን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ አናድርግ ።

፫፻፶ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ የማኅበሩ ፡ አኗኗር ፡ ግን ፡ በብዙ ፡ ወገን ፡ ይጠቅማል ፡ ከርሱ ፡ አንዱ ፡ ለብቻው ፡ የሚኖር ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ሥጋውን ፡ ስመጥቀም ፡ አይችልምና ፤ ሁለተኛው ፡ የመ ሲሀ ፡ ፍቅር ፡ (ወንጌል) የሐዋርያት ፡ ትእዛዝ ፡ ከእኛ ፡ ወገን ፡ ሁሉም ፡ ለብቻው ፡ የሚጠቀም በትን ፡ የሚሻ ፡ እንዳይሆን ፡ ታዝዛለች ፡ እኮ ፡ ወንድሞቹን ፡ በሚጠቅም ፡ ገንዘብ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፫፻፶፩ ዳግመኛም ፡ ባሕታዊ ፡ የራሱን ፡ ሕፀፅ ፡ አያው ቅም ፡ እኮ ፡ አንዲቱን ፡ ትእዛዝ ፡ ለመፈጸም ፡ በተዘጋጀ ፡ ጊዜ ፡ ሲላይቱ ፡ ነገር ፡ ታመልጠዋ ለች ፡ ሕመምተኛውን ፡ በጎበኘ ፡ ጊዜ ፡ እንግዳ ፡ መቀበሉ ፡ ያመልጠዋል ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ሀብት ፡ መቀበል ፡ እንደ፡ት ፡ ይቻለዋል ? ይህች፡ ግን ፡ ባልንጀራውን ፡ ለመርዳት ፡ እንደሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ፈጽሞ ፡ አትሰጠውም ፡ በተቀበ ላትም ፡ ጊዜ ፡ በራሱ ፡ ተሠውራ ፡ ትኖራለች ፡ ባልንጀራውም ፡ አይጠቀምባትም ፡ እርሱም ፡ ከባልንጀራው ፡ አይጠቅምባትም ፡ ከማኅበሩ ፡ አንድነት ፡ ግን ፡ ሁሉ ፡ ለእያንዳንዱ ፡ የራሱ ፡ ሐብት ፡ የባልንጀራው ፡ ሐብት ፡ ይበቃዋልና ።

፫፻፶፪ ባሕታዊ ፡ ግን ፡ ቢተኛ ፡ የሚቀሰቅሰው ፡ አያገ ኝም ፡ ከወንድሞች ፡ ምስጋና ፡ ተጨምሮለት ፡ በትሩፋት ፡ ፀንቶ ፡ ስመኖር ፡ በጉባዔ ፡ ተመ ክሮ ፡ የሚያገኘውን ፡ ዋጋ ፡ አያገኝም ፡ ምንም ፡ እርሱ ፡ ሕፁፅ ፡ ቢሆን ፡ ወደ ፡ ትሩፋት ፡ ፍጻም ነት ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ያስባል ፡ እርሱ ፡ የሚራራ ለት ፡ የሚዋረድለት ፡ ስላላገኘ ፡ የርኅራኄና ፡ የትሕትና ፡ ሥራ ፡ ይፈጽም ፡ ዘንድ ፡ አይቻለ ውም ፡ ፈቃዱን ፡ የሚቋቋምበት ፡ ሰው ፡ ከሌለ፡ እንደ፡ት ፡ ልበ ፡ ሰፊ ፡ ይሆናል ? ።

፫፻፶፫ ትሩፋት ፡ ለመሥራት ፡ ታስተምረው ፡ ዘንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ትጠቅመዋለች ፡ እኮ ፡ ቢልም ፡ ፈጽ

ምር ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይመስል ፡ ከመ ፡ ብእሲ ፡ ዘይሜህር ፡ ጸሪበ ፡ ወኢርእየ ፡ ግብራ ፡ በግብር ፡ ግሙራ ።

፫፻ ፶፬ ዘኒቅያ ፡ ወለእመ ፡ በላዕከ ፡ ሥጋ ፡ በደዌከ ፡ ዕቅፍተ ፡ ይከውነከ ። ወባሕቱ ፡ ኢይትኈለቍ ፡ ውስተ ፡ ኃጢእት ፡ እላ ፡ ኀዘን ፡ በእንተ ፡ ዘኮነ ፡ ዝንቱ ፡ ሕጸጽ ፡ ለትሩፋቲከ ።

፫፻ ፶፭ ወሶበ ፡ እገበረከ ፡ በጊዜ ፡ ደዌከ ፡ ከመ ፡ ትትሐፀብ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ብለኔ ፡ ምዕረ ፡ ወካዕበ ፡ ተሐፀብ ፡ እመሰ ፡ ኮንከ ፡ ጥዑየ ፡ አንተ ፡ ኢትፍቅድ ፡ ተሐፅቦ ፡ በቤተ ፡ ብለኔ ፡ ግሙራ ።

፫፻ ፶፮ ወኢትብኪ ፡ ፈድፋደ ፡ ዘየዐዱ ፡ እምወሰን ፡ ወኢትክላሕ ፡ ፈድፋደ ፡ ወዘምር ፡ በመጠን ፡ ከመ ፡ ኢይዘንግዐ ፡ እኅው ።

፫፻ ፶፯ ወሶበ ፡ ተፈልጠ ፡ ኵሉ ፡ ለለ፩ዱ ፡ ውስተ ፡ መካኑ ፡ እምድኅረ ፡ ፍጻሜ ፡ ጸሎት ፡ ዘይጼልያ ፡ ምስለ ፡ እኅው ፡ ወተከሀሎ ፡ ከመ ፡ ይፈጽም ፡ ትእዛዘ ፡ ሐዋርያ ፡ ዘይቤ ፡ "ጸልዩ ፡ ዘእንበለ ፡ ዕርዓት ፡ ወእእኵቱ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ" ፡ ለይግበር ።

፫፻ ፶፰ በደስ ፡ ፴ወ፰ቱ ፡ እመቦ ፡ ዘፈቀደ ፡ ፍጻሜ ፡ ይፁር ፡ ኵሎ ፡ ሕማመ ፡ እንተ ፡ ትመጽእ ፡ በእንተ ፡ እግዚእብሔር ፡ ወይኩን ፡ ድልወ ፡ ለመዊት ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ እስመ ፡ ኢይትነደግ ፡ ዘእንበለ ፡ ይትመከር ፡ ዘየኀሥሥ ፡ ፍጻሜ ፡ በከመ ፡ ተመከረ ፡ እግዚእነ ፡ በስስዕት ፡ ወትዕቢት ፡ ወፍቅረ ፡ ንዋይ ። ወሶበ ፡ ኢነቅሐ ፡ ወኢተዘከሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ ውእቱ ፡ ይወድቅ ፡ ውስተ ፡ እምልኮ ፡ ጣዖት ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ትዕቢት ።

፫፻ ፶፱ ወሳብዕኒ ፡ በእንተ ፡ ግብር ፡ እንተ ፡ ትደሉ ፡ ከመ ፡ ይትገሠጹ ፡ በእንቲአሃ ። ዘኒቅያ ፡ ወለእመቦ ፡ ዘኮነ ፡ እምእኅው ፡ ዘየአቢ ፡ እመብልዕ ፡ ዘማእደ ፡ ማኅበር ፡ ወረሰዩ ፡ ልማደ ፡ ከመ ፡ ያስተዳልዉ ፡ ሎሙ ፡ ዘይፈቅዱ ፡ ያኅድግዎሙ ፡ ዘንተ ። ወለእመ ፡ አስተዋደይዎሙ ፡ ለሊቀ ፡ ምኔት ፡ ወለመነኰሳት ፡ በእንተ ፡ መብልዕ ፡ ለይኅድጉ ፡ ዘንተ ፡ ግብረ ። ወእመሰ ፡ ኮነ ፡ ዝንቱ ፡ በእንተ ፡ ስስዕት ፡ ወፍትወት ፡ ይትኰነኑ ፡ በከመ ፡ ይደልዎሙ ።

፬፻ ወለእመ ፡ ተጋአዙ ፡ ፪ቱ ፡ እኅው ፡ በምንትኒ ፡ ግብር ፡ ወዘበጠ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ለካልኡ ፡



ሞ ፡ ሥራውን ፡ በሥራ ፡ ሳያይ ፡ ጠራቢነትን ፡ እንደሚያስተምር ፡ ሰው ፡ እርሱ ፡ ይመስላልና፡ ማወቅ ፡ ይገባዋል ።

፫፻ ፶፬ ኒቅያ ፡ በደዌህ ፡ ጊዜ ፡ ሥጋ ፡ ብትበላ ፡ መስናከል ፡ ይሆንብሃል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ኃጢአት፡ ሁኖ እይቆጠርም ፡ ይህ ፡ ለትሩፋትህ ፡ መሰናከል ፡ ስለሆነ ፡ እዘን ፡ እንጂ ።

፫፻ ፶፭ በታመምህ ፡ ጊዜ ፡ ፍል ፡ ውሀ ፡ ገብተህ ፡ ትታጠብ ፡ ዘንድ ፡ ባገበረህ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ጊዜና ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ታጠብ ፡ እንተ ፡ ጤነኛ ፡ ብትሆን ግን ፡ በፍል ፡ ውሀ ፡ ፈጽሞ ፡ መታጠብን ፡ አትውደድ ።

፫፻ ፶፮ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ልቅሶ ፡ እታልቅስ ፡ ፈጽሞ ፡ አትጩኽ ፡ ወንድሞች ፡ እንዳይዘኑ ፡ በመጠን ፡ አመስግን ።

፫፻ ፶፯ ሁሉ ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ከወንድሞች ፡ ጋር ፡ የሚጸልዩት ፡ ከተጨረሰ ፡ በኋላ ፡ ከቦታው ፡ ቢለይ ፡ ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ "ሳታቋርጡ ፡ ጸልዩ ፡ በጊዜያቱም ፡ ሁሉ ፡ እመስግኑ" ያለውን ፡ ትእዛዝ ፡ መፈጸም ፡ ቢቻለው ፡ ይጸልይ ። (፩ ፡ ተሰ ፭ ፡ ፲፯ - ፲፰) ።

፫፻ ፶፰ በደስ ፡ ፴፰ ፡ ፍጹምነትን ፡ የሚወድ ፡ ቢኖር ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ የምት መጣውን ፡ መከራ ፡ ሁሉ ፡ ይቀበል ። በጊዜው ፡ ሁሉ ፡ ለመሞት ፡ ዝግጁ ፡ ይሁን ፡ ጌታችን ፡ በስስት ፡ በትዕቢት ፡ በፍቅረ ፡ ንዋይ ፡ እንደተፈተነ ፡ ፍጹምነትን ፡ የሚሻ ፡ ሳይፈተን ፡ እይቀርምና ፡ በጊዜው ፡ ሁሉ ፡ ባይነቃ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ባያስበው ፡ በጣዖት ፡ አምልኮ ፡ እርሱ ፡ ይወድቃል ፡ ይህችውም ፡ ትዕቢት ፡ ናት ።

፫፻ ፶፱ ሰባተኛውም ፡ በርሷ ፡ ይመከሩ ፡ ዘንድ ፡ ስለምትገባው ፡ ሥራ ፡ ይናገራል ። ኒቅያ ፡ ከወንድሞች ፡ ወገን ፡ ማኅበሩ ፡ የሚመገቡትን ፡ ምግብ፡ አልበላም ፡ የሚል ፡ ቢኖር ፡ የፈለጉትን ፡ ያዘጋጁላቸው ፡ ዘንድ ፡ ልማድ ፡ ቢያደርጉላቸው ፡ ይህን ፡ ያስተዋቸው ። ስለምግብ ፡ አበ ፡ ምኔቱንና ፡ መነኰሳቱን ፡ ቢከሷቸው ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ ይተዉ ፡ ይህ ፡ ስለ ፡ ስስት ፡ ስለ ፡ መጓጓት ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ እንደሚገባቸው ፡ ይቀጡ ።

፬፻ በማናቸውም ፡ ሥራ ፡ ፪ ፡ ወንድማማቾች ፡ ቢጣሉ ፡ ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ ሁለተኛውን ፡ ቢመ

ወኅደገ ፡ ዘተዘብጠ ፡ እበሳሁ ፡ ለያእምር ፡
ኀዳጊ ፡ ጽድቆ ፡ ወይኩን ፡ ዘባጢሁ ፡ ውጉዘ ፡
እስከ ፡ ፵ ፡ ዕለት ። ወእመሰ ፡ ፈደዮ ፡ ለካልኡ ፡
ድኅረ ፡ ወዘበጦ ፡ ይትወገዝ ፡ ውእቱኒ ፡ ከማሁ ።

፩፻፩ ወኵሉ ፡ እምአኃው ፡ ዘሰፍሐ ፡ እዴሁ ፡ ላዕለ ፡
ሊቀ፡ምኔት ፡ ለዘቢጥ ፡ ይዝብጥዎ ፡ ፵ ፡ ዝብጠተ ፡
ወይሰደድ ፡ ኀበ ፡ ካልእ ፡ ምኔት ፡ ወይጹም ፡
ውስቴቱ ፡ ወይንጻሕ ፡ በንስሓ ፡ ዓመተ ፡
ፍጹመ ፡ ወኢይደመር ፡ ወእምድኅረ ፡ ፍጻሜ ፡
ዓመት ፡ ይትመየጥ ፡ ኀበ ፡ ምኔቱ ። ወእመኒ ፡
ኮነ ፡ እምአእሩግ ፡ ምኔት ፡ ቀዳማውያን ፡ ለትት
ኈለቍ ፡ መዓርጉ ፡ ኀበ ፡ ዘይቴሐት ፡ መዓርግ ፡
ዘውስተ ፡ ምኔት ።

፩፻፪ ወኵሉ ፡ እኁ ፡ ዘየሐምዮ ፡ ለቢጹ ፡ እው ፡ ዘያስ
ተዋድዮ ፡ ይፃእ ፡ እምኔት ፡ ወኢይኅድር ፡ ውስ
ቴቱ ፡ ሶበ ፡ ተዐውቀ ፡ ቦቱ ፡ ዝንቱ ፡ ነገር ።

፩፻፫ ወከማሁ ፡ ዘየሐሥም ፡ ላዕለ ፡ መነኰሳት ፡ ወዘ
ይወዲ ፡ ሀከከ ፡ ማእከሌሆሙ ፡ ወዘኒ ፡ ኢይሰ
ምዕ ፡ ወኢይትኤዘዝ ፡ ወዘይትሀከይ ፡ እምግብር
በዕብሬቱ ፡ በጊዜ ፡ ተገብሮ ፡ በፈቃደ ፡ ርእሱ ፡
ወዘያጠፍእ ፡ መብልዐ ፡ አኃው ፡ ወኵሉ ፡ እኁ ፡
ዘይትረከብ ፡ በሰካር ፡ ይኅድጉ ፡ ሎቱ ፡ ምዕረ ፡
ወካዕበ ፡ ወሣልሰ ። ወእመሰ ፡ ኢተመይጠ ፡
ይኩንንዎ ፡ በእንተ ፡ እበሳሁ ፡ ወኢይደሉ ፡
አዝልፎ ፡ ሰትየ ፡ ወይን ፡ ግሙራ ።

፩፻፬ ወኵሉ ፡ እኁ ፡ ጥዑየ ፡ ሥጋ ፡ ዘኢይትጌበር ፡
ይብላዕ ፡ በባሕቲቱ ፡ ንስቲተ ፡ እመብልዕ ፡
እምካልእኒሁ ። ወከማሁ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘያበ
ዝኅ ፡ ነዊመ ፡ በጊዜ ፡ ጸሎት ። ወኵሉ ፡ እኁ ፡
ዘይትዐቀፍ ፡ በግብረ ፡ ዝሙት ፡ ይትኀደግ ፡
ሎቱ ፡ ምዕረ ። ወይጹም ፡ ፵ ፡ ዕለተ ፡ እንዘ ፡
ውጉዝ ፡ ውእቱ ፡ በተሐርሞ ፡ ወንጽሕ ፡ ዓመተ ፡
ፍጹመ ።

፩፻፭ ወለእመ ፡ ወፅአ ፡ እኁ ፡ እምኔቱ ፡ መኒኖ ፡ ሕገ ፡
ምንኵስናሁ ፡ ወሖረ ፡ ኀበ ፡ ሀገር ፡ ወብሔር ፡
ከመ ፡ ይንበር ፡ ህየ ። ይኩን ፡ በመዓርገ ፡ ሕዝ
ባውያን ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡ ውስቴታ ፡ ወኢይደልዎ
ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይትመሰል ፡ በመነኰሳት ፡ ዘአን
በለ ፡ አምሳለ ፡ ሕዝባውያን ፡ ለእመ ፡ ውእቱ ፡
ኢይክል ፡ ላዕለ ፡ ተጸውሮተ ፡ እርእየ ፡ ምንኵ
ስናሁ ፡ ይከውን ፡ ሐሜት ፡ ኀበ ፡ ኵሎሙ ፡



ታው ፡ የተመታው ፡ በደሉን ፡ ቢተው ፡ የተ
ወው ፡ ክብሩን ፡ ይወቅ ፡ የተማታው ፡ እስከ ፡
አርባ ፡ ቀን ፡ የተለየ ፡ ይሁን ። ከመታው ፡
በኋላ ፡ ባልንጀራውን ፡ መልሶ ፡ ቢመታው ፡
ግን ፡ እርሱም ፡ እንደርሱ ፡ ይለይ ።

፩፻፩ ከወንድሞች ፡ ወገን ፡ ለመማታት ፡ በአበ ፡ ም
ኔቱ ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ የዘረጋ ፡ ሁሉ ፡ አርባ ፡ ግር
ፋት ፡ ይግረፉት ፡ ወደሌላ ፡ ገዳምም ፡ ይሰደድ ፡
በውስጡም ፡ ይጹም ፡ ዓመቱን ፡ ፈጽሞ ፡ በንስ
ሐ ፡ ይንጻ ፡ አይገናኝ ፡ ዓመቱ ፡ ከተፈጸመ ፡
በኋላ ፡ ወደገዳሙ ፡ ይመለስ ። ከገዳሙ ፡ ታላ
ላቅ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ወገንም ፡ ቢሆን ፡ መዓ
ርጉ ፡ በገዳሙ ፡ ካለው ፡ መዓርግ ፡ ከዝቅተኛው ፡
ይቆጠር ።

፩፻፪ ባልንጀራውን ፡ የሚያማ ፡ ወይም ፡ የሚከሰው ፡
ወንድም ፡ ሁሉ ፡ ከገዳሙ ፡ ይውጣ ፡ ይህ ፡
ነገር ፡ በታወቀ ፡ ጊዜ ፡ ከገዳሙ ፡ አይደር ።

፩፻፫ እንደዚሁም ፡ በመነኰሳቱ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ የሚያ
ደርግ ፡ በመካከላቸውም ፡ ጠብን ፡ የሚያነሣ ፡
የማይሰማ ፡ የማይታዘዝ ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡
በሥራ ፡ ጊዜ ፡ በሰሞኑ ፡ ሥራውን ፡ ችላ ፡
የሚል ፡ የወንድሞችን ፡ ምግብ ፡ የሚያባክን ፡
ሰክሮ ፡ የሚገኝ ፡ ወንድም ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡
ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ይተውት ፡ ባይመ
ለስ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ በደሉ ፡ ይቅጡት ፡ ወይን ፡
መጠጣትን ፡ ማዘውተር ፡ ፈጽሞ ፡ አይገባ
ውም ።

፩፻፬ የሥጋ ፡ ጤነኛ ፡ የሆነ ፡ የማይሠራ ፡ ወንድም ፡
ሁሉ ፡ ከወንድሞቹ ፡ ተለይቶ ፡ ከመብል ፡
ወገን ፡ ብቻውን ፡ ጥቂት ፡ ይብላ ፡ በጸሎት ፡
ጊዜ ፡ እንቅልፍ ፡ የሚያበዛም ፡ ቢሆን ፡ እንደ
ዚሁ ፡ ነው ፡ በዝሙት ፡ ሥራ ፡ የሚስነካከል ፡
ወንድም ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይቀርለታል ፡
ዓመት ፡ ሙሉ ፡ በንስሓና ፡ በንጽሕና ፡ የተለየ ፡
ሁኖ ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ ይጹም ።

፩፻፭ መነኵሴ ፡ የምንኵስናውን ፡ ሕግ ፡ ንቆ ፡ ከገ
ዳሙ ፡ ቢወጣ ፡ በዚያ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ወደከ
ተማና ፡ ወደገጠርም ፡ ቢሄድ ፡ በዚያች ፡ ውስጥ ፡
ባሉት ፡ በሕዝባውያን ፡ መዓርግ ፡ ይኑር ፡ በሕ
ዝባውያን ፡ አምሳላ ፡ እንጂ ፡ መነኰሳቱን ፡
ይመስል ፡ ዘንድ ፡ አይገባውም ። አርሱ ፡ የምን
ኵስናውን ፡ እርእያ ፡ መከተል ፡ ባይችል ፡ በመ
ነኰሳቱ ፡ ሁሉ ፡ ሐሜት ፡ ይሆናል ፡ ከፉ ፡ ስም

መንኰሳት ፡ ወይሬሲ ፡ ሎሙ ፡ ስመ ፡ እኩየ ፡
ወዝንቱ ፡ አንቀጽ ፡ ዘእንበለ ፡ ግዘት ።

፩፻፷፮ በስ ፡ ፴ወ፪ቱ ፡ ወዘይነብር ፡ እምዕሙዳን ፡ ምስለ
ብእሲት ፡ ወይብል ፡ ዝንቱስ ፡ ግብር ፡ ኢያጼ
ስረኒ ፡ ይትፈለጡ ፡ ፪ሆሙ ። አው ፡ ይኩኑ ፡
ውጉዛነ ፡ እስመ ፡ መጽሐፍ ፡ ይቤ ፡ "መኑ ፡
ውእቱ ፡ ዘየዐቀር ፡ እሳተ ፡ ውስተ ፡ ሕፅኑ ፡
ወኢይውዒ" ፡ ወመጸሕፍት ፡ ቅዱሳት ፡ ይሜህ
ራነ ፡ ከመ ፡ ንትጎነፆ ፡ እምቀረበ ፡ አንስት ፡
ፈድፋደ ፡ ወእምተናግሮቶን ፡ ከማሁ ፡ ተዓቀቡ ፡
ጥቀ ።

፩፻፷፯ ሳምን ፡ በእንተ ፡ መነኮሳይያት ፡ ወመበለታት ፡
ዕሙዳት ። ረስጣ ፡ ፲ወ፯ቱ ፡ ይቤ ፡ ጴጥሮስ ፡
"ለይሠይማ ፡ ሠላስ ፡ መበለታት ፡ ወ፪ቲ ፡ እም
ኔሆን ፡ ይፀመዳ ፡ ለጸሎት ፡ በእንተ ፡ ኵሎሙ ፡
እለ ፡ ሀለዉ ፡ ውስተ ፡ መከራ ፡ ወይፈቅዱ ፡
ከመ ፡ ይትከሠት ፡ ሎሙ ፡ ዘይከውን" ። ወሣ
ልሲትኒ ፡ ትንብር ፡ ኀበ ፡ አንስት ፡ አለ ፡ ይመ
ጽኣ ፡ ወይረውፃ ፡ ኀበ ፡ ድዉያን ፡ ከመ ፡ ይትለ
አካ ፡ ሠናየ ፡ ወይንቅሓ ፡ ወያጠይቃ ፡ ለቀሳው
ስት ፡ ዘይከውን ። ወኢትኩን ፡ መፍቀሪተ ፡
ረባኅ ፡ ወኢትስክር ፡ ከመ ፡ ኢይትሀከያ ፡ ለመ
ልእክተ ፡ ሌሊት ።

፩፻፷፰ ዘ፷ወ፮ቱ ፡ ወሶበ ፡ ተሠይመት ፡ መበለት ፡ ዕቤር ፡
ኢይቅብእዋ ፡ አላ ፡ ይሢምዋ ፡ በስም ፡ ባሕ
ቲቱ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ምታ ፡ ዘሞተ ፡ እምዘ
መን ፡ ብዙኅ ፡ ለትሠየም ። ወለእመሰ ፡ ኮነ ፡
ዘሞተ ፡ በቅሩብ ፡ ኢይእመንዋ ፡ ዳእሙ ፡ እመ
በጽሐት ፡ ኀበ ፡ ርስእና ፡ ለትትመከር ፡ ፩ደ ፡
ዘመነ ። ወይሢምዋ ፡ በቃል ፡ ባሕቲቱ ፡ ወያቅ
ንትዋ ፡ ምስለ ፡ እለ ፡ ተርፉ ፡ ዕቤራት ። ወኢያን
ብሩ ፡ ላዕሌሃ ፡ እደ ፡ እስመ ፡ ይእቲ ፡ ኢታዐርግ ፡
ቍርባነ ፡ ወአልባቲ ፡ መልእክት ፡ እስመ ፡ ሶት
በትስ ፡ ይከውን ፡ ውስተ ፡ ሶዩም ፡ በእንተ ፡
መልእክት ። ወለሰቢርስ ፡ በእንተ ፡ ጸሎት ፡
ወዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ ለለ፩ዱ ።

፩፻፷፱ ፷ወ፯ቱ ፡ ወኢይንብሩ ፡ እደ ፡ ላዕለ ፡ ርእሰ ፡ ድን
ግል ፡ አላ ፡ ሕሊናሃ ፡ ለባሕቲታ ፡ እንተ ፡ ትሬ
ስያ ፡ ድንግለ ።

፩፻፸ ድስቅ ፡ ፲ወ፬ቱ ፡ ወትሠየም ፡ መበለት ፡ ዘኮነ ፡
መዋዕሊሃ ፡ ፷ ፡ ዓመት ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ላቲ ፡
ጽንዕ ፡ ከመ ፡ ኢትትወሰብ ፡ ዳግመ ፡ ወታመ



ስምም ፡ ያወጣላቸዋል ፡ ይህ ፡ ያልተወገዘበት ፡
አንቀጽ ፡ ነው ።

፩፻፷፮ በስ ፡ ፴፪ ፡ ከመነኰሳት ፡ ወገን ፡ ከሴት ፡ ጋር ፡
የሚኖር ፡ ይህ ፡ ሥራ ፡ ድል ፡ አይነሣኝም ፡
የሚል ፡ ሁለቱም ፡ ይለያዩ ፡ ወይም ፡ የተለዩ ፡
ይሁኑ ። "መጽሐፍ ፡ በጭኑ ፡ እሳት ፡ ቋጥሮ ፡
የማይቃጠል ፡ ማነው ? ብሏልና" (ምሳ ፡ ፮ ፡ ፳፯)
ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትም ፡ ፈጽሞ ፡ ሴትን ፡ ከመ
ቅረብና ፡ ከመነጋገር ፡ እንርቅ ፡ ዘንድ ፡ ያስተ
ምሩናል ፡ (፩ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፩) ። እንደዚሁ ፡ ፈጽማ
ችሁ ፡ ተጠንቀቁ ።

፩፻፷፯ ስምንተኛው ፡ ስለሴቶች ፡ መነኰሳትና ፡ ፍጹ
ማን ፡ ስለሆኑ ፡ ባልቴቶች ፡ ይናገራል ። ረስጣ ፡
፲፯ ። ጴጥሮስ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ሦስት ፡ መነኰ
ሳይያት ፡ ይሾሙ ፡ ከእነርሱም ፡ ሁለቱ ፡ በመከራ ፡
ውስጥ ፡ ስላሉ ፡ ስዎችና ፡ የሚሆነውም ፡ ይገለጽ
ላቸው ፡ ዘንድ ፡ ስለሚወዱ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡
ለጸሎት ፡ ይትጉ ። ሦስተኛዋም ፡ የታመሙትን ፡
ከሚረዱና ፡ ከሚጠይቁ ፡ ሴቶች ፡ ዘንድ ፡
ትኑር ፡ በጎ ፡ አገልግሎትን ፡ ያገለግሉ ፡ ዘንድ ፡
የነቁ ፡ ይሁኑ ፡ የሚሆነውንም ፡ ለቀሳውስት ፡
ያስረዱ ፡ እርሷ ፡ ጥቅምን ፡ ፈላጊ ፡ አትሁን ፡
ለሌሊቱ ፡ አገልግሎት ፡ እንዳይስንፉ ፡ እርሷ ፡
አትስከር ።

፩፻፷፰ ፷፮ ፡ ባልቴቲቱ ፡ መነኰሲት ፡ ብትሾም ፡ በቅብ
ዓት ፡ አይሾሟት ። በስም ፡ ብቻ ፡ ይሾሟት ፡
እንጂ ፡ ባሏ ፡ ከሞተ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ቢሆን ፡
ትሾም ፡ ባሏ ፡ ከሞተ ፡ ጥቂት ፡ ዘመን ፡ ቢሆን ፡
ግን ፡ እምነው ፡ አይሾሟት ፡ ወደ ፡ እርጅና ፡
የደረሰች ፡ እንደሆነች ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ትፈ
ተን ፡ እንጂ ፡ በቃል ፡ ብቻ ፡ ይሾሟት ፡ ከቀ
ሩት ፡ ባልቴቶች ፡ ጋር ፡ እንድትረዳ ፡ ያድርጓት
እጅ ፡ አይጫኑባት ፡ ይህች ፡ መሥዋዕት ፡ አት
ሠዋምና ፡ ሥልጣንም ፡ የላትምና ፡ ማማተብስ ፡
ሥልጣን ፡ ላላቸው ፡ ሾማምት ፡ ነውና ፡ ለባል
ቴቲቱ ፡ ግን ፡ በጸሎት ፡ ይሁን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡
ለእያንዳንዱ ፡ ነው ።

፩፻፷፱ ፷፯ ፡ በድንግሊቱ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ እጅ ፡ አይጫኑ ፡
ድንግል ፡ የምታደርጋት ፡ አሳቧ ፡ ብቻ ፡ ናት ፡
እንጂ ።

፩፻፸ ድስቅ ፡ ፲፬ ፡ ዕድሜዋ ፡ ፷ ፡ ዓመት ፡ የሆናት ፡
መነኰሲት ፡ ትሾም ፡ ኃይል ፡ ይሆንላት ፡ ዘንድ ፡
ዳግመኛም ፡ እንዳታገባ ፡ በመነኰሳቱም ፡

አንቀጽ ፡ ፲ ።

ጽእ ፡ ኀሣረ ፡ ሳዕለ ፡ ክብረ ፡ መበለታት ። በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ኢይደሉ ፡ ለወራዛዊት ፡ ከመ ፡ ትትሀወክ ፡ ዳእሙ ፡ ከመ ፡ ትጽናዕ ፡ ሠናየ ። ወክዋኖታሂ ፡ ከመ ፡ ኢትብፃዕ ፡ ሠናይ ፡ ላቲ ፡ እምዘትበፅዕ ፡ ወኢትፈጽም ፡ ብፅዐታ ። ወኢይጽሐፍዋ ፡ ለወራዛዊት ፡ መበለት ፡ ውስተ ፡ መዓርገ ፡ ዕቤራት ፡ መበለታት ፡ ከመ ፡ ኢትትመዋዕ ፡ እምድኅረ ፡ ጠባይዓሃ ፡ በእንተ ፡ ናእሰ ፡ ዘመና ፡ ወኢትትወሰብ ፡ ዳግመ ፡ ወኢትኩን ፡ ሰላቀ ፡ ለሰይጣን ።

፩፻፲፭ በደሰ ፡ ፱ቱ ፡ ወክብረ ፡ መበለታትሰ ፡ በፍድፋዴ ፡ ጸሎት ፡ ወተልእኮተ ፡ ድውያን ፡ ወአብዝኆተ ፡ ጾም ። በሰ ፡ ፺ወ፫ቱ ፡ ወይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩና ፡ ደናግል ፡ ውስተ ፡ መዓርግ ፡ ቀዳማዊ ፡ ወመበለታት ፡ ውስተ ፡ መዓርግ ፡ ዳግማዊ ።

፩፻፲፮ ወለእመ ፡ ኮነት ፡ እሐቲ ፡ ብእሲት ፡ ዘሞተ ፡ ምታ ፡ ትንበር ፡ ምስለ ፡ ዕቤራት ፡ ወሶበ ፡ ኢፈቀደት ፡ ይእቲ ፡ ትንበር ፡ ምስሌሆን ፡ ወትትወሰብ ፡ ለካልእ ፡ ብእሲ ፡ እምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ይከውና ፡ ላቲ ፡ ኀቢአተ ፡ ወኵነኔ ፡ ዐቢየ ።

፩፻፲፯ ወይደልዎን ፡ ለዕቤራት ፡ ከመ ፡ ኢያብዝኃ ፡ ሰሐቀ ፡ ወኢይንበራ ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ ዘሀሎ ፡ ባቲ ፡ ተባዕት ፡ ዘእንበለ ፡ እኅሆን ፡ ወእቡሆን ፡ ወውሉዶን ። ወኢይደሉ ፡ ለዕቤራት ፡ ወለደናግል ፡ የሐልያ ፡ ለፍትወተ ፡ ሥጋሆን ፡ ወይደልዎን ፡ ከመ ፡ ይጹማ ፡ ኵሎ ፡ ዕለተ ፡ በዘይከላ ፡ እጥፍአ ፡ ነደ ፡ ትፍግዕታት ፡ ወይክህላ ፡ ተጸብአ ፡ ለዕድዋኒሆን ፡ ወይደልዎን ፡ ለደናግል ፡ ከመ ፡ ይትዓቀባ ፡ ፈድፋደ ።

፩፻፲፰ ወኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ትሑር ፡ እሐቲ ፡ ባሕቲታ ፡ ድኅረ ፡ በጽሐት ፡ ለዓቅመ ፡ ተወስቦ ። ወኢይደሉ ፡ ለድንግል ፡ ከመ ፡ ታስተርኢ ፡ ግሙራ ፡ ለሰብእ ፡ እምድኅረ ፡ ዕርበተ ፡ ፀሐይ ፡ ወኢትስተይ ፡ ወይነ ፡ ግሙራ ፡ ዘእንበለ ፡ ትኩን ፡ ሕምምተ ፡ በብዙኅ ፡ ገድል ። ወኢታማዝፍ ፡ ሥጋሃ ፡ ፈድፋደ ፡ ዘይበዝኅ ፡ እምወሰን ። ወመብልዕሰ ፡ ንዋየ ፡ ሐቅሉ ፡ ለትፍግዕት ፡ ይእቲ ። ወብሕትውናሰ ፡ ጥንተ ፡ ማእሰራ ፡ ይእቲ ፡ ለንጽሕና ።

፩፻፲፱ አለሰ ፡ የበውዳ ፡ እመካን ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ ኢይድኅና ፡ እምንጻሬ ፡ ዓይን ፡ እው ፡ እምሰሚዐ ፡ ዕዝን ፡ እው ፡ እምሐሜተ ፡ ልሳን ፡ እለ ፡

ስለ ፡ መነኰሳት ።

ክብር ፡ ላይ ፡ ውርደትን ፡ ታመጣለች ። ስለዚህ ፡ ወጣቲቱ ፡ መታወክ ፡ አይገባትም ፡ በበጎ ፡ ምግባር ፡ ትጽና ፡ እንጂ ፡ አኳኋኗም ፡ ስዕለቷን ፡ ከተሳለች ፡ በኋላ ፡ ብፅዓቷን ፡ እንዳታፈርስ ፡ ነው ፡ ወጣቲቱን ፡ መነኰሲት ፡ በባልቴቶቹ ፡ መነኰሳይያት ፡ መዓርግ ፡ አይጸፏት ፡ ዘመኗ ፡ ስላነስ ፡ በስውነቷ ፡ ይከማኅት ፡ ድል ፡ እንዳትነሣ ፡ ዳግመኛም ፡ እንዳታገባ ፡ የሰይጣንም ፡ መዘባበቻ ፡ እንዳትሆን ።

፩፻፲፭ በደስ ፡ ፱ ፡ የመነኰሳይያቱ ፡ ክብር ፡ ግን ፡ ጸሎትን ፡ በማብዛት ፡ ድውዮችን ፡ በማገልገል ፡ ጾምን ፡ በማብዛት ፡ ነው ። በሰ ፡ ፺፫ ፡ ደናግል ፡ በመጀመሪያው ፡ መዓርግ ፡ መሆን ፡ ይገባቸዋል ፡ ባልቴቶችም ፡ በሁለተኛው ፡ መዓርግ ፡ ይሁኑ ።

፩፻፲፮ ባሏ ፡ የሞተባት ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ብትኖር ፡ ከባልቴቶቹ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ልትኖር ፡ ባትወድ ፡ ሌላ ፡ ባል ፡ ታግባ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ታላቅ ፡ ኀቢአትና ፡ ቅጣት ፡ ይሆንባታል ።

፩፻፲፯ ባልቴቶች ፡ ሣቅ ፡ እንዳያበዙ ፡ ይገባቸዋል ፡ ወንድ ፡ ካለበት ፡ ቦታ ፡ አይቀመጡ ፡ ከወንድማቾው ፡ ከአባታቸው ፡ ከልጆቻቸው ፡ በቀር ፡ ባልቴቶችና ፡ ደናግል ፡ ለሥጋቸው ፡ ፈቃድ ፡ ማሰብ ፡ አይገባቸውም ። የፈተናን ፡ ፆር ፡ ማጥፋት ፡ በሚችሉ ፡ ገንዘብ ፡ ሁልጊዜ ፡ መጾም ፡ ይገባቸዋል ፡ ባላጋሮቻቸውን ፡ ለመጣላት ፡ ይችሉ ፡ ዘንድ ፡ ደናግል ፡ ዘወትር ፡ ይጠበቁ ፡ ዘንድ ፡ ይገባቸዋል ።

፩፻፲፰ አካለ ፡ መጠን ፡ ከደረሰች ፡ በኋላ ፡ አንዲቱ ፡ ብቻዋን ፡ መሄድ ፡ አይገባትም ፡ ድንግል ፡ ፀሐይ ፡ ከገባ ፡ በኋላ ፡ ፈጽሞ ፡ ለሰው ፡ መታየት ፡ አይገባትም ፡ በገድል ፡ ብዛት ፡ የታመመች ፡ ካልሆነች ፡ በቀር ፡ ፈጽሞ ፡ ወይን ፡ አትጠጣ ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ፈጽሞ ፡ ሥጋዋን ፡ አታድንድን ። መብል ፡ ለዝሙት ፡ መሣሪያው ፡ ነው ፡ ብቸኝነት ፡ ግን ፡ ለንጽሕና ፡ የማሠሪያዋ ፡ መጀመሪያ ፡ ናት ።

፩፻፲፱ ከቦታ ፡ ወደቦታ ፡ የሚዞሩ ፡ ግን ፡ በዓይን ፡ ከማየት ፡ በጆሮ ፡ ከመስማት ፡ በአንደበት ፡ ከማማት ፡ አይድኑም ። ወደልብ ፡ ባዕምን ፡ የሚ

እማንቱ ፡ ያበጽሓ ፡ ኀበ ፡ ልብ ፡ ጣዕመ ፡ ወይእት ዓቀባ ፡ አምዕርዓት ፡ ወእምሀኬት ፡ እስኳ ፡ ያረ ኵሳ ፡ ለሳናቲሆን ፡ በሐሜት ፡ ወበነገረ ፡ ጕሕ ሉት ፤ በእንተዝ ፡ ኢይሰመያ ፡ ዕቤራተ ፡ ወይ ናግለ ።

፬፻፲፮ ወኢይደልዋ ፡ ለድንግል ፡ ከመ ፡ ታልዕል ፡ ቃላ ፡ አንዘ ፡ ትትናገር ፡ ወኢትትበአስ ፡ ወኢ ትትፋታሕ ፡ በእንተ ፡ ንዋያተ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም። እስመ ፡ ይእቲ ፡ መነንት ፡ ዓለመ ፡ ወይእቲ ፡ አመተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢትኩንኒ ፡ አመተ ፡ ለንዋየ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ወየእከላ ፡ ግብረ ፡ እደ ዊሃ ፡ ለሕይወተ ፡ ዚአሃ ፡ በተባሕትዎ ፡ ውስተ ፡ ቤታ ። ወኢይደልዋ ፡ ከመ ፡ ትባእ ፡ ውስተ ፡ ግብረ ፡ ሁከት ፡ ወሓልዮ ፡ ዓለማዊ ። እው ትሑር ፡ ኀበ ፡ መካነ ፡ ከብካብ ፡ ወኢትብጻሕ ፡ ኀበ ፡ ጉባኤ ፡ ግሙራ ፡ ወይደልዋ ፡ ከመ ፡ ታል ምድ ፡ ልሳና ፡ በአንብቦተ ፡ መዝሙራት ፡ ወከመ ፡ ትኩን ፡ ንጽሕተ ፡ ወተእዛዚተ ፡ ወት ሕተ ፡ በነገራ ፡ ወየዋሂተ ፡ እምእከይ ፡ ወመዝ ለፈተ ፡ ተፀምዶ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ላቲ ፡ ጥበብ ፡ በኵሉ ፡ ሠናያት ። ወትፀመድ ፡ ለጸሎት ፡ ወት ጋሀ ፡ በኵሉ ፡ ሌሊት ፡ እስመ ፡ ንዋም ፡ ሥሩዕ ፡ ውእቱ ፡ ለሥጋ ፡ ጠባይዓዊ ። ወባሕቱ ፡ እብ ዝኖ ፡ ንዋም ፡ ውፁእ ፡ ውእቱ ፡ አምጠባይዐ ፡ ሥጋ ።

፬፻፲፯ ወኢያልብስ ፡ ብእሲ ፡ ወለቶ ፡ ልብሰ ፡ አስ ኬማ ፡ አንዘ ፡ ድንግል ፡ ይእቲ ፡ እላ ፡ ይእቲ ፡ ትብፃዕ ፡ በርእሳ ፡ ከመ ፡ ሶበ ፡ ወድቀት ፡ ትኩን፡ ግብረ ፡ ኃጢአት ፡ ገባኢተ ፡ ሳዕሌሃ ፡ ለባሕ ቲታ ።

፬፻፲፰ ድስቅ ፡ ፲ወ፩ቱ ፡ ወይኩና ፡ ዕቤራት ፡ ዘአንበለ ፡ ቍጥዓ ፡ ወኢያብዝኃ ፡ ነገረ ፡ ወኢይኩና ፡ ሐማ ይያተ ፡ ወኢይስምዓ ፡ ነገረ ፡ እኩየ ።

፬፻፲፱ ዘ፳ወ፩ቱ ፡ ወትኩን ፡ ድንግል ፡ ንጽሕተ ፡ በነ ፍሳ ፡ ወበሥጋሃ ። እስመ ፡ ይእቲ ፡ መቅደሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወማኅደረ ፡ ክርስቶስ ፡ ወም ዕራፈ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ።



የመጡ ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፡ ሥራ ፡ ከመፍታት ፡ ከስንፍና ፡ ያጠበቁ ፡ በሐሜትና ፡ በሽንገላ ፡ ነገር ፡ እንደበታቸውን ፡ የሚያረክሱ ፡ ማን ፡ ስለ ዚህ ፡ ባልቴቶችና ፡ ይናግል ፡ አይባሉም ።

፬፻፲፮ ድንግል ፡ ስትናገር ፡ ቃሏን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ማድረግ ፡ አይገባትም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ገንዘብ ፡ አትጣላ ፡ አትከራከር ፡ እርሷ ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ንቃለችና ፡ እርሷም ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገልጋይ ፡ ናት ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ገንዘብ ፡ አገልጋይ ፡ አትሁን ። በብቸኝነት ፡ በቤቷ ፡ ውስጥ ፡ ለርሷ ፡ ሕይወት ፡ የእጅዋ ፡ ሥራ ፡ ይበቃታል ። ወደጠብና ፡ ወደ ዓለማዊ ፡ ሐሳብ ፡ መግባት ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሠርግ ፡ ቦታ ፡ መሄድ ፡ አይገባትም ፡ ወደአደባ ባይ ፡ ፈጽሞ ፡ አትድረስ ፡ እንደበቷን ፡ ዳዊት ፡ በመድገም ፡ ማስለመድ ፡ ይገባታል ፡ ንጽሕት ፡ ታዛዥ ፡ በነገሯ ፡ ትሑት ፡ ከክፋት ፡ የራቀች ፡ እንልማስትንም ፡ የምታዘወትር ፡ ትሁን ፡ ዘንድ ፡ በጎ ፡ ሥራን ፡ ሁሉ ፡ ማስተዋል ፡ ያሆ ንላት ፡ ዘንድ ፡ ለጸሎት ፡ ለስግደት ፡ በሌሊቱ ፡ ሁሉ ፡ ትትጋ ፡ እንቅልፍ ፡ ለሥጋ ፡ ተፈጥሮ ፡ የታዘዘ ፡ ነውና ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እንቅልፍ ፡ ማብ ዛት ፡ ከሥጋ ፡ ተፈጥሮ ፡ የወጣ ፡ ነው ።

፬፻፲፯ አባት ፡ ልጁን ፡ ድንግል ፡ ሁና ፡ ሳለች ፡ የምን ኵስና ፡ ልብስ ፡ አያልብሳት ፡ እርሷ ፡ ትሳል ፡ እንጂ ፡ በኃጢአት ፡ ሥራ ፡ በወደቀች ፡ ጊዜ ፡ በራሷ ፡ ብቻ ፡ ይፈረድባት ፡ ዘንድ ።

፬፻፲፰ ድስቅ ፡ ፲፩ ፡ ባልቴቶች ፡ ያለቁጣ ፡ ይኑሩ ፡ ነገር ፡ አያብዙ ፡ ሐሜተኞችም ፡ አይሁኑ ፡ ክፉ ፡ ነገርንም ፡ አይስሙ ።

፬፻፲፱ ፳፩ ፡ ድንግል ፡ በነፍሷና ፡ በሥጋዋ ፡ ንጽሕት ፡ ትሁን ፡ የእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ የክርስ ቶስ ፡ ማደሪያ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ማረፊያ ፡ ናትና ።

---

## አንቀጽ ፡ ፲ወ፮ ።

በእንተ ፡ ተማኅጽ ፡ ወትእዛዘ ፡ ሕዝባውያን ፡ ወማኅበረ ፡ ኵሎሙ ፡ ምእመናን ።

## አንቀጽ ፡ ፲፮ ።

ስለ ፡ ሕዝባውያን ፡ ትእዛዝና ፡ ምክር ፡ ስለምእ መናን ፡ ሁሉ ፡ አንድነት ፡ ይናገራል ።

፬፻፳ ወውእቱ ፡ ፫ቱ ፡ እክፋል ። ክፍል ፡ ቀዳማዊ ፡ ዘተነግረ ፡ ላዕለ ፡ ኵሎሙ ፡ ሕዝብ ፡ ወውእቱ ፡ ላዕለ ፡ ፪ቱ ፡ ግብራት ። ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ትምህርት ፡ መሢሐዊት ፡ ዘሀለወት ፡ በወንጌል ፡ ወበመልእክት ፡ ሐዋርያዊት ፡ ወናሁ ፡ ተነግረ ፡ በእንቀጽ ፡ ፺ወ፰ቱ ።

፬፻፳፩ ወዳግምኒ ፡ ዘተነግረ ፡ በቀኖናት ፡ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ተነግረ ፡ በጥንተ ፡ ዲድስቅልያ ፡ ተዐቀቡ ፡ እደቂቀ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ትግበሩ ፡ ኵሎ ፡ ዘያበጽሐከሙ ፡ ኀበ ፡ ተእዝዞ ፡ እግዚአብሔር ።

፬፻፳፪ ወእመቦ ፡ ዘየሐውር ፡ ፩ዱሂ ፡ ውስተ ፡ ገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይትቃረን ፡ ፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይትኌለቍ ፡ ምስለ ፡ ዕልው ፡ ዓለማዊ ፡ ስስል ፡ እምኵሉ ፡ ዓመፃ ፡ ወእምፍቅረ ፡ ክፍል ፡ ዘየዐዚ ። ወኢትወስክ ፡ ኀብረ ፡ ዲበ ፡ ኀብርከ ፡ ዘወሀበከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኪያሁ ፡ እመ ፡ ልደትከ ፡ ኢትሕዕን ፡ ሥዕርተከ ፡ ከመ ፡ ይኑኅ ፡ ወኢትዕቀቦ ፡ ዘእንበለ ፡ ተላጽዮ ፡ ወኢ፡ተሠንዮ ፡ ከመ ፡ ያምጽእ ፡ ኀቤከ ፡ እንስተ ፡ ዘቅሩብ ፡ መሥገርቶን ።

፬፻፳፫ ኢትልበስ ፡ አልባስ ፡ ቀጠንተ ፡ እስመ ፡ ይእቲ ፡ ታመጽእ ፡ ስሕተተ ፡ ወኢትሠእን ፡ እሣእነ ፡ ዕሉለ ፡ በማዕለል ፡ ወኢሕልቀተ ፡ ወርቅ ፡ ውስተ ፡ አጻብዒከ ። እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ ትእምርተ ፡ ዝሙት ፡ ውእቱ ። ወኢትግበር ፡ ሥዕርተከ ፡ ፍቱሐ ፡ ወዝርዙረ ፡ ወኢፅፉረ ። ወኢትንሣእ ፡ እምጸጕረ ፡ ጽሕምከ ፡ ወኢታማስና ፡ ወኢይወልጥ ፡ ብእሲ ፡ አርአያሁ ፡ እምጠባይዓሁ ፡ እስመ ፡ ሕግ ፡ ከልአ ፡ እምዝንቱ ፡ ኵሉ ።

፬፻፳፬ ዘ፪ቱ ፡ ወለእመ ፡ ኮንከ ፡ ባዕለ ፡ ዘኢትፈቅድ ፡ ኀበ ፡ ኪን ፡ ዘተሐፄ ፡ ቦቱ ፡ ኢትኩን ፡ ዘእንበለ ፡ ጥበብ ። ወሶበ ፡ ወፃእከ ፡ እምቤትከ ፡ ኩን ፡ ምስለ ፡ ምእመናን ፡ ወተናገር ፡ ምስሌሆሙ ፡ ነገረ ፡ ሕይወት ።

፬፻፳፭ ወይደልወከሙ ፡ ከመ ፡ ትኅድጉ ፡ እከየ ፡ ማእከሌከሙ ፡ ወትሥረዩ ፡ ፍጡነ ፡ ኃጢአተ ፡ አኃዊከሙ ፡ ወአኮ ፡ ዘንብል ፡ ዘንተ ፡ በእንተ ፡ መኳንንት ። ወንሕነ ፡ ንመክረከሙ ፡ ከመ ፡ ትግበሩ ፡ ሠናያተ ፡ ኵሎ ፡ ጊዜ ፡ ወትንሥኡ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ ክብረ ፡ ብዙኀ ፡ ዘኢይትኌለቍ ።



፬፻፳ የኛውም ፡ ሦስት ፡ ክፍል ፡ ነው ። መጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ በሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ የተነገረ ፡ ነው ፡ ከእነርሱም ፡ አንዱ ፡ በወንጌል ፡ በሐዋርያት ፡ መልእክት ፡ ያለች ፡ የመሢሕ ፡ ትምህርት ፡ ናት ፡ እነሆ ፡ በአርባ ፡ አምስተኛው ፡ አንቀጽ ፡ ተነገረ ።

፬፻፳፩ ሁለተኛው ፡ በመጽሐፍ ፡ የተነገረ ፡ ነው ። ከዚህ፡ በኋላ ፡ በዲድስቅልያ ፡ መጀመሪያ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወደመታዘዝ ፡ የሚያደርሳችሁን ፡ ሁሉ ፡ ትሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ተጠበቁ ፡ ተብሎ ፡ ተነገረ ።

፬፻፳፪ አንዱስ ፡ እንኳ ፡ ኃጢአት ፡ ለመሥራት ፡ የሚሄድ ፡ ቢኖር ፡ እርሱ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፈቃድ ፡ ይጠላልና ፡ ከዓለማዊ ፡ መናፍቅም ፡ ጋር ፡ ይቆጠራል ፡ ከበደል ፡ ሁሉና ፡ ከፍተኛውን ፡ ክፍል ፡ ከመውደድ ፡ ሁሉ ፡ ሽሽ ። በተፈጠርህ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰጠህ ፡ መልክ ፡ ላይ ፡ መልክ፡ አትጨምር ። ያድግ ፡ ዘንድ ፡ ፀጉርህን ፡ አትከባከበው ፡ ተላጨው ፡ እንጂ ፡ አታሳድገው ። ወጥመዳቸው ፡ ቅርብ ፡ የሆነ ፡ ሴቶችን ፡ ወደ አንተ ፡ ያመጣብህ ፡ ዘንድ ፡ አታሳምረው ።

፬፻፳፫ ረቂቅ ፡ ልብስ ፡ አትልበስ ፡ ይህች ፡ ስሕተትን ፡ ታመጣለችና ፡ ቀለም ፡ የተቀባ ፡ ጫማ ፡ አትጫማ ፡ በጣቶችህ ፡ የወርቅ ፡ ቀለበትን ፡ አታድርግ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ የዝሙት ፡ ምልክት ፡ ነውና ። ጠጉርህን ፡ ግልስልስ ፡ ብጥር ፡ አታድርገው ፡ አትሥራው ፡ የጢምህን ፡ ጠጉር ፡ አትቈረጥ ፡ አትላጨው ፡ ሰው ፡ መልኩን ፡ ከተፈጥሮው ፡ አይለውጥ ፡ ሕግ ፡ ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ከልክሏልና ።

፬፻፳፬ ፪ ፡ የምትኖርበትን ፡ ጥበብ ፡ የማትሻ ፡ ባለጸጋ ፡ ከሆንክ ፡ ያለ ፡ ጥበብ ፡ አትኑር ፡ ከቤትህ ፡ በወጣህ ፡ ጊዜ ፡ ከምእመናን ፡ ጋር ፡ ሁን ፡ ከእነርሱም ፡ ጋር ፡ የሕይወትን ፡ ነገር ፡ ተነጋገር ።

፬፻፳፭ በመካከላችሁ ፡ ያለውን ፡ ጠብ ፡ የወንድማችሁን ፡ ኃጢአት ፡ ፈጥኖ ፡ ይቅር ፡ ማለት ፡ ይገባችኋል ፡ ይህን ፡ ማለታችን ፡ ስለዳኞች ፡ አይደለም ። እኛ ፡ ዘወትር ፡ በጎ ፡ታደርጉ ፡ ዘንድ ፡ እንመክራችኋለን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የማይቆጠር ፡ ብዙ ፡ ክብርን ፡ ታገኙ ፡ ዘንድ ።

አንቀጽ ፡ ፲፩ ።

፩፻፷፮ ወእመ ፡ ተዳደቀክሙ ፡ ፈቃደ ፡ ሰይጣን ፡ ከመ ፡
ትትመበዑ ፡ ኢታዕርቡ ፡ ፀሐየ ፡ ላዕለ ፡ መዓ
ትክሙ ፡ ይቤ ፡ ሰሎሞን ፡ "እስመ ፡ ነፍስ ሙ ፡
ለእለ ፡ ይዜክሩ ፡ እከየ ፡ ትረክብ ፡ ሞተ ። ወእ
ግዚእኒ ፡ አዘዘነ ፡ ከመ ፡ ናፍቅር ፡ ጸላእተነ ፡
እፎኬ ፡ ንጸልእ ፡ ፍቁራኒነ" ።

፩፻፷፯ ዘ፲ወ፩ዱ ፡ ወለእመ ፡ ፈቀድከ ፡ ከመ ፡ ትኩን ፡
መሢሐዌ ፡ ትሉ ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወፍ
ታሕ ፡ ማእሰራተ ፡ እከይ ፡ እምላዕሌከ ።

፩፻፷፰ ዘ፲ቱ ፡ እለሰ ፡ ይገብሩ ፡ ተጋእዞ ፡ ወተቃውሞ ፡
ወተፋትሖ ፡ ነኪራን ፡ እሙንቱ ፡ እምእግዚአብ
ሔር ። እስመ ፡ አምላክ ፡ ምሕረት ፡ ውእቱ ።
ወእምቀዳሚ ፡ ጸውዐ ፡ ሕዝበ ፡ ለንስሓ ፡ እመ
ንገለ ፡ ጻድቃን ፡ ወነቢያት ፡ ወቅዱሳን ።

፩፻፷፱ ወለእለ ፡ ኮኑ ፡ እምቅድመ ፡ ማየ ፡ አይኅ ፡ ኮነ ፡
ይሜህሮሙ ፡ እመንገለ ፡ አቤል ፡ ወሴት ፡ ወሄ
ኖስ ፡ ወሄኖክ ፡ ዘፈለሰ ፡ ወለእለ ፡ ነበሩ ፡ በጊዜ ፡
ማየ ፡ አይኅ ፡ ሰበኮሙ ፡ እመንገለ ፡ ኖኅ ። ወለ
እለ ፡ ነበሩ ፡ ውስተ ፡ ሰዶም ፡ ሰበኮሙ ፡ እመን
ገለ ፡ ሎጥ ፡ አንጻረ ፡ ኢንግዳ ።

፩፻፸ ወለእለ ፡ ነበሩ እምድኅረ ፡ አይኅ ፡ መሀሮሙ ፡
እመንገለ ፡ መልከጼዴቅ ፡ ወአብርሃም ፡ ዐቢመ
ፍቀሬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢዮብ ። ወለግብጻውያ
ንሂ ፡ ሰበኮሙ ፡ በሙሴ ፡ ወለደቂቀ ፡ እስራ
ኤል ፡ መሀሮሙ ፡ እመንገለ ፡ ሙሴ ፡ ወኢያሱ ፡
ወልደ ፡ ነዌ ፡ ወካሌብ ፡ ወፊንሐስ ፡ ወእምድኅ
ሬሆሙኒ ፡ መሀሮሙ ፡ በመላእክት ፡ ወነቢ
ያት ።

፩፻፸፩ ወለእለ ፡ ኮኑ ፡ እምቅድመ ፡ ምጽአቱ ፡ ኮነ ፡
ይሰብኮሙ ፡ እመንገለ ፡ ዮሐንስ ፡ ሰባኪሁ ።
ወለእለ ፡ ነበሩ ፡ ድኅረ ፡ ምጽአቱ ፡ ሰበኮሙ ፡
ለሊሁ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ "ነስሑ ፡ ነዋ ፡ ቀርበት ፡
መንግሥተ ፡ ሰማያት" ። ወለእለ ፡ ነበሩ ፡ እም
ድኅረ ፡ ሕማሙ ፡ በሥጋ ፡ ዘሐመ ፡ በእንቲአነ ፡
ሰበኮሙ ፡ እመንገሌነ ፡ ንሕነ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ሐዋር
ያት ፡ ወጳውሎስ ፡ ዘኮነ ፡ ንዋየ ፡ ኅሩየ ።

፩፻፸፪ ወዘሰ ፡ ይትጌበር ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ፡ በገዘ
ንቱ ፡ ዘመን ፡ ኀላፊ ፡ ወይትሀከይ ፡ በእንተ ፡
ግብር ፡ ዘለዓለም ፡ ወያስተሐምም ፡ ከርሦ ፡
ዕለተ ፡ በጽሕቅ ፡ ለመብልዕ ፡ ዘይጠፍእ ፡ ወይ
ትገደፍ ፡ ወይሜንኖ ፡ ለዘአልቦቱ ፡ ተፍጻሜት ፡

ስለ ፡ ሕዝባውያን ፡ ተግሣጽ ።

፩፻፷፮ ትጣሉ ፡ ዘንድ ፡ የሰይጣን ፡ ፈቃድ ፡ ቢያነሣሣ
ችሁ ፡ ፀሐይ ፡ ሳይገባ ፡ ይቅር ፡ ተባባሉ ። ሰሎ
ሞን ፡ «ቂምን ፡ የያዙ ፡ ሰዎች ፡ ሰውነት ፡ ክፉ ፡
ሞትን ፡ ታገኛለችና ፡ አለ» ጌታችንም ፡ ጠላቶ
ቻችንን ፡ እንወድ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘን ። (ማቴ ፡ ፭ ፡
፵፭) ። ወዳጆቻችንንማ ፡ እንዴት ፡ እንጠላለን ?

፩፻፷፯ ፲፩ ፡ ክርስቲያን ፡ ልትሆን ፡ ከወደድኽ ፡ የእግ
ዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ ተከተል ፡ ከሰውነትህም ፡
የክፋትን ፡ ማሠሪያ ፡ አርቅ ።

፩፻፷፰ ፲ ፡ የሚባሉ ፡ የሚከራከሩ ፡ የሚጣሉ ፡ ሰዎች ፡
ግን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተለዩ ፡ ናቸው ፡ እርሱ ፡
የይቅርታ ፡ ባለቤት ፡ ነውና ፡ በመጀመሪያ ፡
ከጻድቃን ፡ ከቅዱሳን ፡ ነቢያት ፡ ወገን ፡ ሕዝ
ቡን ፡ ለንስሓ ፡ ጠራ ።

፩፻፷፱ ከማየ ፡ አይኅ ፡ (ከጥፋት ፡ ውሃ) ፡ አስቀድሞ ፡
ለነበሩት ፡ ሰዎች ፡ በአቤል ፡ በሴት ፡ በሄኖስ ፡
በተሠወረው ፡ በሄኖክ ፡ አድሮ ፡ ያስተምራ
ቸው ፡ ነበር ፡ በማየ ፡ አይኅ ፡ ጊዜ ፡ ለነበሩትም ፡
በኖህ ፡ አድሮ ፡ አስተማራቸው ፡ በሰዶም ፡ ለነ
በሩት ፡ ሰዎችም ፡ እንግዳን ፡ በሚቀበል ፡ በሎጥ
አድሮ ፡ አስተማራቸው ።

፩፻፸ ከጥፋት ፡ ውኃ ፡ በኋላ ፡ ለነበሩት ፡ ሰዎች ፡ በመ
ልከ ፡ ጼዴቅ ፡ በአብርሃምና ፡ እግዚአብሔርን ፡
በሚወድ ፡ በኢዮብ ፡ አድሮ ፡ አስተማራቸው ።
ግብጻውያንንም ፡ በሙሴ ፡ አስተማራቸው ፡ የእ
ሥራኤልን ፡ ልጆች ፡ በሙሴ ፡ በነዌ ፡ ልጅ ፡
በኢያሱ ፡ በካሌብ ፡ በፊንሐስ ፡ አድሮ ፡ አስተ
ማራቸው ። ከእነርሱም ፡ በኋላ ፡ በመላእክት ፡
በነቢያት ፡ አስተማራቸው ።

፩፻፸፩ ከመምጣቱ ፡ አስቀድሞ ፡ ለነበሩ ፡ ሰዎች ፡ በሰ
ባኪው ፡ በዮሐንስ ፡ አድሮ ፡ ያስተምራቸው ፡
ነበር ። ከመጣ ፡ በኋላ ፡ የነበሩትን ፡ ሰዎች ፡
ራሱ ፡ እነሆ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ቀርባ
ለች ፡ ንስሓ ፡ ግቡ ፡ እያለ ፡ አስተማራቸው ።
(ማቴ ፡ ፬ ፡ ፲፯) ስለእኛ ፡ በሥጋ ፡ ታሞ ፡ ከሞተ ፡
በኋላ ፡ የነበሩትን ፡ ሰዎች ፡ በእኛ ፡ በ፲፪ቱ ፡
ሐዋርያት ፡ ምርጥ ፡ ዕቃ ፡ በሆነው ፡ በጳውሎስ
አድሮ ፡ አስተማራቸው ።

፩፻፸፪ በዚህ ፡ በኀላፊው ፡ ዘመን ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡
የሚሠራ ፡ ስለዘለዓለሙ ፡ ሥራ ፡ ቸል ፡ የሚል ፡
ለሚጠፋው ፡ ለሚቀረው ፡ መብል ፡ ሁልተን ፡
በትጋት ፡ የሚያስብ ፡ ፍጻሜ ፡ የሌለበትን ፡
ግን ፡ የሚንቀውን ፡ ሰው ፡ ከአንተስ ፡ አሕዛብ ፡

ሎቱ ፡ እሩኑ ፡ ዘኢይበልዎ ፡ ሎቱ ፡ እስመ ፡ አሕዛብ ፡ ይጸድቁ ፡ ፈድፋደ ፡ እምኔክ ፡ በከመ ፡ ጸአላ ፡ እግዚእነ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ወይቤላ ፡ እስመ ፡ ሰዶም ፡ ጸድቀት ፡ ፈድፋደ ፡ እምኔኪ ፡ ምንትኑ ፡ ትሠጠዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘትዴኀር ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ቅድስት ።

፩፻፴፫ ወኪያሆሙስ ፡ ለምእመናን ፡ ሎሙ ፡ ይእቲ ፡ ጥበብ ፡ ወተግባሮሙኒ ፡ አምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ። ወግበሩኬ ፡ ኪነተክሙ ፡ ከመ ፡ ትጠበቡ ፡ በከመ ፡ ልማድ ፡ ለሲሲትክሙ ። ወተፀመዱ ፡ በተቀንዮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በምግባር ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ "ኢትትግበሩ ፡ ለመብልዕ ፡ ዘይማስን ። ዳእሙ ፡ ለመብልዕ ፡ ዘይከውን ፡ ለሕይወት ፡ ዘለዓለም" ፡ ወይቤ ፡ ካዕበ ፡ "ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ግብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ትእመኑ ፡ በዘፈነዎ ፡ ውእቱ" ።

፩፻፴፬ ዘ፳ወ፬ቱ ፡ ወኢይደሉ ፡ ለነ ፡ ንሕነ ፡ ምእመናን ፡ ከመ ፡ ንኩን ፡ ሰሩዓነ ፡ ወኢንኩን ፡ ከማትያነ ፡ ምሥጢር ፡ አላ ፡ ንኩን ፡ ጽኑዓነ ፡ በተሰናእዎ ። እስመ ፡ እግዚእነ ፡ አዘዘነ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ "ኢትደዩ ፡ ባሕርየክሙ ፡ ቅድመ ፡ አሕርው" ። ወሶበ ፡ ይሰምዑ ፡ እለ ፡ ኢየአምኑ ፡ ነገረነ ፡ ዘበእንተ ፡ ክርስቶስ ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ በተጸንሶቶሙ ፡ እምአእምሮተ ፡ ሃይማኖት ፡ ይሳለቁ ፡ ላዕሌነ ፡ ወይመስሎሙ ፡ ከመ ፡ ሐሰት ፡ ውእቱ ፡ ወነዋ ፡ ይቤ ፡ አሌ ፡ ሎቱ ፡ ለዘይፀርፍ ፡ ላዕለ ፡ ስምየ ፡ በእንቲአሁ ፡ በውስተ ፡ አሕዛብ ።

፩፻፴፭ ዘ፳ወ፭ቱ ፡ ወኵሉ ፡ ዘይረግም ፡ በከንቱ ፡ ይረግም ፡ ነፍሶ ። ወንሕነ ፡ ንሜህሮሙ ፡ ለመበለታት ፡ ወለደካትም ፡ ከመ ፡ ይንሥኡ ፡ ዘፈነወ ፡ ሎሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ በአኰቴት ፡ ወበፍርሃት ።

፩፻፴፮ ዘ፳ወ፮ቱ ፡ ወተፈለጡ ፡ እምእለ ፡ ዩገብሩ ፡ እኩየ ፡ ከመ ፡ ዘይትጎነሥ ፡ እምእለ ፡ ይቀትሉ ፡ ነፍሰ ፡ እው ፡ እምዘማውያን ፡ ከመ ፡ ኢይበሉክሙ ፡ እስመ ፡ ክርስቲያን ፡ ይትፌሥሑ ፡ በምግባር ፡ ዘትትሀደዋ ፡ ለሕግ ። ወአኮ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘይፈቅድ ፡ ተራድኦተነ ፡ ዳእሙ ፡ ንሕነ ፡ ንፈቅድ ፡ ምሕረተ ፡ ዚአሁ ። ወዘይፈቅዶስ ፡ እምኔነ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ለነ ፡ ነቢር ፡ በሃይማኖት ፡ ወግቢር ፡ ከመ ፡ ፈቃዱ ።

፩፻፴፯ ዘ፳ወ፯ቱ ፡ ንመክረክሙ ፡ አ ፡ አኃዊነ ፡ ወሱታፊነ ፡ ውስተ ፡ አምልኮ ፡ ከመ ፡ ትትየዩ ፡ እም



ይሻላሉ ፡ እኮ ፡ እንደምን ፡ አይሉትም ? ጌታችን ፡ ኢየሩሳሌምን እንደሰደባት ፡ «ከአንቺ ፡ ይልቅ ፡ ፈጽሞ ፡ ሰዶም ፡ ገሞራ ፡ ትሻላለች ፡ እኮን» (ማቴ ፡ ፲፩ ፡ ፳፫) አላት ። ከቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ወደኋላ ፡ የምትል ፡ አንተ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምን ፡ ትመልስለታለህ ?

፩፻፴፫ የምእመናን ፡ ብልሃታቸው ፡ ግን ፡ ይህች ፡ ጥበብ ፡ ናት ፡ ሥራቸውም ፡ እግዚአብሔርን ማምለክ ፡ ነው ፡ ምግባችሁን ፡ ለማግኘት ፡ እንደ ፡ ልማድ ፡ ትራቀቁ ፡ ዘንድ ፡ ብልሃታችሁን ፡ አድርጉ ። ለእግዚአብሔር ፡ በመገዛት ፡ በሥራ ፡ ትጉ ፡ ጌታችን ፡ «ለጠፊው ፡ ምግብ ፡ አትሥሩ ፡ ለዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ ለሚሆነው ፡ መብል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንዳለ» (ዮሐ ፡ ፮ ፡ ፳፯) ዳግመኛም ፡ "የእግዚአብሔር ፡ ሥራ ፡ እርሱ ፡ በላከው ፡ ታምኑ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ አለ" ። (ዮሐ ፡ ፮ ፡ ፳፱) ።

፩፻፴፬ እኛ ፡ ምእመናን ፡ ሥራ ፡ ፈቶች ፡ መሆን ፡ አይገባንም ፡ በመመራመር ፡ የጸናን ፡ እንሁን ፡ እንጂ ፡ ምሥጢር ፡ አባካኞች ፡ አንሁን ፡ ጌታችን ፡ "ዕንቋችሁን ፡ ከእጎርው ፡ ባሕርይ ፡ አትጣሉምሩ" (ማቴ ፡ ፯ ፡ ፯) ሲል ፡ አዝዞናልና ፡ የማያምኑ ፡ ሰዎች ፡ ስለክርስቶስ ፡ የምናስተምረውን ፡ ነገራችንን ፡ በስሙ ፡ ጌዜ ፡ ሃይማኖትን ከለማወቅ ፡ የተነሣ ፡ ተቸግረዋልና ፡ ይዘብቱብናል ፡ እርሱ ፡ እንደ ፡ ሐሰት ፡ ይመስላቸዋል ። እነሆ ፡ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ ስሜን ፡ የሚሳደብ ፡ ሰው ፡ ወዮለት ፡ አለ ።

፩፻፴፭ ፳፭ ፡ በከንቱ ፡ የሚረግም ፡ ሁሉ ፡ ራሱን ፡ ይረግማል ፡ እኛ ፡ በምስጋናና ፡ በፍርሃት ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰጣቸውን ፡ ይቀበሉ ፡ ዘንድ ፡ ባልቴቶችንና ፡ ደካሞችን ፡ እናስተምራቸዋለን ።

፩፻፴፮ ፳፮ ፡ ነፍስ ፡ ከሚገድሉ ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ ከዘማውያን ፡ እንደሚለይ ፡ ሰው ፡ ክፉ ፡ ከሚያደርጉ ፡ ሰዎች ፡ ተለዩ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሕግን ፡ በሚያፈርስ ፡ ሥራ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፡ እኮ ፡ እንዳይሉ።ችሁ ። ክርስቶስ ፡ የኛን ፡ ርዳታ ፡ የሚሻ ፡ አይደለም ፡ እኛ ፡ የርሱን ፡ ይቅርታ ፡ እንሻለን ፡ እንጂ ። እርሱ ፡ ከእኛ ፡ የሚሻው ፡ በሃይማኖት ፡ በንተን ፡ ፈቃዱን ፡ እንፈጽም ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

፩፻፴፯ ፳፯ ፡ በአምልኮ ፡ ወንድሞቻችንና ፡ ተባባሪዎቻችን ፡ ሆይ ፡ ከሥራ ፡ ፈትነት ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡

ነገር ፡ ፅሩዕ ፡ ወእምነገር ፡ እኩይ ። ወእም ፡ ንባበ ፡ ኀፍረት ፡ ወእምነገር ፡ ሕሡም ፡ ወእም ስካር ፡ ወእምስስዕት ። ወኢይደሉ ፡ ለክሙ ፡ ፍጹመ ፡ ከመ ፡ ትትናገሩ ፡ ነገረ ፡ ዘኢይረብኅ ። አው ፡ ትግበሩ ፡ ዘኢይሤኒ ፡ ፈድፋደስ ፡ በዕ ለተ ፡ እሑድ ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ትት ፈሥሑ ፡ ፍሥሐ ፡ መንፈሳዊተ ።

፩፻፴፰ ረስጣ ፡ ፰ቱ ፡ ይቤ ፡ ጴጥሮስ ፡ ኢትትናገር ፡ ላዕለ ፡ ፩ዱ፡ሂ ፡ ነገረ ፡ እኩየ ፡ ወኢተሐሊ ፡ ከመ፡ ትግበር ፡ እኩየ ፡ ላዕለ ፡ መኑሂ ፡ ወኢትኩን ፡ ዘ፪ኤ ፡ ልቡ ፡ ወኢዘ፪ኤ ፡ ልሳኑ ፡ ወኢትኩን ፡ መፍቀሬ ፡ ክፍል ፡ ዐቢይ ፡ ወኢትምክር ፡ ምክረ ፡ እኩየ ።

፩፻፴፱ ወይቤ ፡ እንድርያስ ፡ ኢትኩን ፡ ቀናኤ ፡ ወኢመ ስተሳልቀ ። ወኢመፍቀሬ ፡ ቀትል ፡ ወኢመዓ ትመ ፡ እስመ ፡ ቍጥዓ ፡ ያበጽሕ ፡ ኀበ ፡ ቀትል ።

፩፻፵ ዘ፱ቱ ፡ ይቤ ፡ ፊልጶስ ፡ ኢትኩን ፡ ፈታዌ ፡ እስመ ፡ ፍትወት ፡ ይስሕብ ፡ ኀበ ፡ ዝሙት ፡ ወሶበ ፡ ተደመረ ፡ ሰይጣነ ፡ መዓት ፡ ምስለ ፡ ሰይጣነ ፡ ፍትወት ፡ ያነኑልዎ ፡ እሙንቱ ፡ ለዘ ይትዌከፎሙ ፡ ወማኅደሩስ ፡ ለመንፈስ ፡ እኩይ፡ ውእቱ ፡ ቍስለ ፡ አበሳሃ ፡ ለነፍስ ። ወሶበ ፡ ረከበ ፡ ሙባአ ፡ ንኡሰ ፡ ውእቱ ፡ ያርኅቦ ፡ ለመ ካን ፡ ወያመጽእሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ መናፍስት ፡ ጸዋጋን ፡ ወያበውእሙ ፡ ኀበ ፡ ይእቲ ፡ ነፍስ ፡ ወኢይትከሀሎ ፡ ለውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ከመ ፡ ይትለዐል ፡ ግሙራ ፡ ወይርአይ ፡ ጽድቀ ።

፩፻፵፩ ዘ፲ ፡ ይቤ ፡ ያዕቆብ ፡ እ ፡ ወልድየ ፡ ኢትሑር ፡ በትእምርታት ፡ ወኢትኩን ፡ ጸዋጌ ፡ ወኢትኩን እምሰብእ ፡ እለ ፡ የዐቅቡ ፡ ሰዓታተ ፡ ወኅራይ ያነ ፡ ዕለታት ፡ ወኢረእዩ ፡ ከዋክብት ፡ ወኢእ ምእለ ፡ ይትፋወሉ ፡ በሐመድ ፡ ወፍሬ ፡ ዕፀው ፡ ወዛጕል ፡ ወኢትፍቶ ፡ ከመ ፡ ታእምር ፡ ዘንተ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ ይወስድ ፡ ኀበ ፡ አምልኮ፡ ጣዖት ።

፩፻፵፪ ፲፩ቱ ፡ ይቤ ፡ ናትናኤል ፡ እ ፡ ወልድየ ፡ ኢትኩን ፡ ሐሳዌ ፡ ወኢመፍቀሬ ፡ ወርቅ ፡ ወኢመፍቀሬ ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ ይወ ስድ ፡ ኀበ ፡ ሰረቅ ። ወኢታንጐርጕር ፡ እስመ ፡ ነጐርጓር ፡ ይወስድ ፡ ኀበ ፡ ፅርፈት ። ወኢትትዐ በይ ፡ ዳእሙ ፡ ተባየጽ ፡ ወአፍቅር ፡ ጻድቃነ ፡ ወትሑታነ ፡ ወኵሎ ፡ ዘረከበከ ፡ ተወከፍ ፡ በአ ኰቴት ።

ከሚያሳፍር ፡ ንግግር ፡ ከሚያስቀይም ፡ ነገር ፡ ከስካር ፡ ከስስት ፡ ትርቁ ፡ ዘንድ ፡ እንመክራች ኋለን ። የማይጠቅም ፡ ወይም ፡ የማያምር ፡ ነገር ፡ ትናገሩ ፡ ዘንድ ፡ ወይም ፡ ትሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ፈጽሞ ፡ አይገባችሁም ። ይልቁንም ፡ መንፈሳ ዊ ፡ ደስታ ፡ ልታደርጉባት ፡ በምትገባው ፡ በዕ ለተ ፡ እሑድ ።

፩፻፴፰ ረስጣ ፡ ፰ ፡ ጴጥሮስ ፡ በአንዱ ፡ ላይስ ፡ እንኳ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አትናገር ፡ በማንም ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ አታስብ ፡ ሁለት ፡ ልብ ፡ አት ሁን ፡ ሁለት ፡ ምላስም ፡ አብልጡልኝ ፡ ማለ ትን ፡ የምትወድ ፡ አትሁን ፡ ክፉ ፡ ምክርም ፡ አትምከር ፡ አለ ።

፩፻፴፱ እንድርያስም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ቀናተኛ ፡ የምት ዘብት ፡ ነፍስ መግደልን ፡ የምትወድ ፡ አትሁን ፡ ቁጣ ፡ ነፍስ ፡ ወደመግደል ፡ ያደርሳልና ።

፩፻፵ ፱ ፡ ፊልጶስ ፡ እንደዚህ ፡ አለ ፡ ፍትወተኛ ፡ አት ሁን ፡ ፍትወት ፡ ወደዝሙት ፡ ያደርሳልና ፡ ሰይ ጣነ ፡ መዓት ፡ ከሰይጣነ ፡ ፍትወት ፡ ጋር ፡ በተገ ናኘ ፡ ጊዜ ፡ የሚቀበላቸውን ፡ እነርሱ ፡ ያጠፉ ታል ፡ የመጥፎ ፡ መንፈስ ፡ ማደሪያ ፡ ግን ፡ የነ ፍስ ፡ የበደል ፡ ቁስልዋ ፡ ነው ። ትንሽ ፡ መግ ቢያ ፡ ያገኘ ፡ እንደሆነ ፡ እርሱ ፡ ቦታውን ፡ ያስ ፋፋዋል ፡ ክፉዎችን ፡ አጋንንትን ፡ ሁሉ ፡ አም ጥቶ ፡ በዚች ፡ ነፍስ ፡ ያሳድራቸዋል ። ስዚህ ፡ ሰው ፡ ፈጽሞ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይል ፡ ዘንድ ፡ ከብር ንም ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡ አይቻለውም ።

፩፻፵፩ ፲ ፡ ያዕቆብም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ በምልክቶች ፡ አትሂድ ፡ ጋኔን ፡ ጠሪ ፡ አት ሁን ፡ ጊዜያቶችን ፡ ከሚጠብቁ ፡ ቀንን ፡ ከሚ መርጡ ፡ ኮከብ ፡ ከሚቆጥሩ ፡ በአመድ ፡ በዕን ጨት ፡ ፍሬ ፡ በዛጕል ፡ ከሚያሟርቱ ፡ ሰዎች ፡ ወገን ፡ አትሁን ፡ ይህን ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፡ አት ውደድ ፡ አለ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ጣዖትን ፡ ወደ ፡ ማም ለክ ፡ ይወስዳልና ።

፩፻፵፪ ፲፩ ፡ ናትናኤል ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ሐሰተኛ ፡ ገንዘብ ፡ ወዳጅ ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ወዳጅ ፡ አትሁን ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ሥርቆት ፡ ይወስዳልና ፡ አታንጐራጕር ፡ ማንጐራጕር ፡ ወደስድብ ፡ ያደርሳልና ። አትኩራ ፡ ወንድሜ ፡ ወንድሜ ፡ ተባባል ፡ እንጂ ፡ ጻድቃንን ፡ ትሁታ ንን ፡ ውደድ ፡ እንጂ ፡ ያገኘሽንም ፡ ሁሉ ፡ በም ስጋና ፡ ተቀበል ፡ እንጂ ።

፩፻፵፫ ዘሰወረኒት ፡ ወምእመናን ፡ ይትመጠዉ ፡ እም
እደ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በበክፍል ፡ እምኀብስት ፡
አሐዱ ፡ ዘአምጽእዎ ፡ እምቅድመ ፡ ይትፌተት፤
እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ኀብስተ ፡ በረከት ፡ ውእቱ ፡
ወአኮ ፡ ቍርባን ።

፩፻፵፬ ዘሰወረኒት ፡ ወለእመ ፡ ኢሀሎ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ይት
መጠዉ ፡ አውሎግያ ፡ እምእደ ፡ ቀሲስ ፡ ወለ
እመ ፡ ኢሀሎ ፡ ቀሲስ ፡ እምእደ ፡ ዲያቆን፡ ይን
ሥኡ ። ወለሕዝባዊሰ ፡ ኢይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይግ
በር ፡ ወየሀብ ፡ አውሎግያ ።

፩፻፵፭ ዘሰወረኒት ፡ ብልዑ ፡ ወስትዩ ፡ በበ ፡ መዓርግ ፡
ወባሕቱ ፡ ኢትስተዩ ፡ እስከ ፡ ትሰክሩ ፡ ከመ ፡
ኢይሳለቁክሙ ፡ ሰብእ ።

፩፻፵፮ ዖቅ ፡ ዘሰወረኒት ፡ ወኢይደልዎ ፡ ለክርስቲያናዊ፤
ከመ ፡ ይሐውር ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ከብካብ ፡ ይጥፋሕ ፡
እደዊሁ ፡ ወያጽሕስ ፡ በእገሪሁ ፡ ዳእሙ ፡ ይብ
ላዕ ፡ በሥርዓት ፡ በከመ ፡ ይደልዎሙ ፡ ለቅዱ
ሳን ።

፩፻፵፯ ዘሰወረኒት ፡ ወኢይደልዎ ፡ ለምእመን ፡ ከመ ፡
ይስተዩ ፡ ውስተ ፡ ቤት ፡ ዘይትጋብኡ ፡ ባቲ ፡
ሰብእ ፡ ሐማዩያን ፡ ወእለ ፡ አልቦሙ ፡ ኂሩት ፡
ወኢስ ፡ ይስትዩ ፡ በቀተት ፡ እስተዋዒእሙ ።

፩፻፵፰ ዘኒትያ ፡ አ ፡ ፋቅር ፡ ኢትሑር ፡ ዘእንበለ ፡ ተዓ
ቅቦ ፡ ወኢትኩን ፡ ዐብደ ፡ አው ፡ ኢኀፋሬ ፡
ወኢትፍቱ ፡ ከመ ፡ ታጥሪ ፡ ለከ ፡ ወርቀ ፡ ወኢ
ብሩረ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘየአክል ፡ ለሕይወትከ ፡ ወለ
ሲሳይከ ፡ ወለልብስከ ፡ በእምጣን ፡ ዘተወስነ ።
ወሕዝባዊ ፡ ሶበ ፡ ጽሕቀ ፡ ከመ ፡ ይንግድ ፡
ውስተ ፡ መካን ፡ ዘአልቦ ፡ ውስቴቱ ፡ ዘርእ ፡
ወኢተግባር ፡ ሠናይ ፡ ውእቱ ፡ ሎቱ ።

፩፻፵፱ ወይኩኑ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ክቡራነ ፡ በኀቤከ ፡
ፈድፋደ ፡ እምነፍስከ ፡ ወተአኅው ፡ ምስለ ፡
ኵሉ ፡ ሰብእ ። ወኢትኩን ፡ መፍቀሬ ፡ ጋእዝ ፡
ወኢትዝብጥ ፡ ፩ደኒ ፡ ዘእንበለ ፡ ሕግ ፡ በእንተ፡
ትምህርት ፡ ወተግሣጽ ፡ ከመ ፡ በዝንቱ ፡ ይትዐ
ቀብ ፡ ድኅረ ፡ ወዝኒ ፡ በተዓቅቦ ፡ ዐቢይ ፡ ከመ ፡
ኢይኩን ፡ ሞቱ ፡ በእዴከ ፡ እስመ ፡ ለሞት ፡
ሎቱ ፡ ምክንያት ፡ ብዙኅ ።

፩፻፶ በደስ ፡ ፅወጀቱ ፡ ወይደልወነ ፡ ከመ ፡ ንኩን ፡
ንቁሓነ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ ወኢ.ነሀብ ፡ ለእዕይን
ቲነ ፡ ንዋመ ፡ ወኢድቃስ ፡ ለቀራንብቲነ ፡
እስከ ፡ ንረከብ ፡ መካነ ፡ ለእግዚአብሔር ።



፩፻፵፫ ፅ፳ ፡ ምእመናን ፡ ሳይቆረስ ፡ ካመጡት ፡ ከአ
ንዱ ፡ ኅብስት ፡ የተቈረሰውን ፡ ከኤጲስቆጶሱ ፡
እጅ ፡ ይቀበሉ ፡ ይህ ፡ ሥጋውና ፡ ደሙ ፡ ያይ
ደለ ፡ የበረከት ፡ እንጀራ ፡ ነውና ።

፩፻፵፬ ፅ፯ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ባይኖር ፡ በረከተ ፡ ኅብስቱን፡
ከቄሱ ፡ እጅ ፡ ይቀበሉ ፡ ቄሱም ፡ ባይኖር ፡ ከዲ
ያቆኑ ፡ እጅ ፡ ይቀበሉ ፡ ሕዝባዊ ፡ ግን ፡ በረከተ፡
ኅብስቱን ፡ ቆርሶ ፡ መስጠት ፡ አይገባውም ።

፩፻፵፭ ፅ፯ ፡ በየመዓርጋችሁ ፡ ብሉ ፡ ጠጡ ፡ ነገር ፡
ግን ፡ እስክትሰክሩ ፡ ድረስ ፡ አትጠጡ ፡ ሰዎች ፡
እንዳይዘብቱባችሁ ።

፩፻፵፮ ዶቅ ፡ ፶፫ ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ወደ ፡ ሠርግ ፡ ቤት ፡
ሂዶ ፡ በእጁ ፡ ማጨብጨብ ፡ በእግሩ ፡ ማሸብ
ሸብ ፡ አይገባውም ፡ ለተከበሩ ፡ ሰዎች ፡ እንደሚ
ገባቸው ፡ በሥርዓት ፡ ይብላ ፡ እንጂ ።

፩፻፵፯ ፶፰ ፡ ምእመን ፡ የሚያሙ ፡ ሰዎች ፡ ከተሰበሰ
ቡበት ፡ ርኅራኄ ፡ የሌላቸው ፡ በውርርድ ፡ እወ
ጣጥተው ፡ የሚጠጡ ፡ ሰዎች ፡ ካሉበት ፡ ቤት ፡
ገብቶ ፡ መጠጣት ፡ አይገባውም ።

፩፻፵፰ ኒቅያ ፡ ወዳጅ ፡ ሆይ ፡ ያለመጠበቅ ፡ አትሂድ ።
ሰነፍ ፡ ወይም ፡ አፋር ፡ አትሁን ፡ ወርቅ ፡ ብር ፡
ትሰበስብ ፡ ዘንድ ፡ አትውደድ ። ለሰውነትህ ፡
ለምግብህ ፡ ለልብስህ ፡ ለተወሰነው ፡ ያህል ፡
የሚበቃህን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሕዝባዊ ፡ ዘርና ፡
ሥራ ፡ በሌለበት ፡ ቦታ ፡ ሊነግድ ፡ በተጋ ፡ ጊዜ፡
ለርሱ ፡ መልካም ፡ ነው ።

፩፻፵፱ ከራስህ ፡ ይልቅ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በአንተ ፡
ዘንድ ፡ ፈጽሞ ፡ የከበሩ ፡ ይሁኑ ፡ ከሰው ፡ ሁሉ፡
ጋር ፡ ወንድሜ ፡ ወንድሜ ፡ ተባባል ፡ ጠብ ፡
ወዳጅ ፡ አትሁን ። ስለ ፡ ትምህርትና ፡ ስለም
ክር ፡ ከሕግናት ፡ በቀር ፡ አንዱንስ ፡ እንኳ ፡ አት
ማታ ፡ ኋላ ፡ በዚህ ፡ ይጠበቅ ፡ ዘንድ ፡ ያኸውም
በፍጹም ፡ ጥንቃቄ ፡ ይሁን ፡ ሞቱ ፡ በእጅህ ፡
እንዳይሆን ፡ ለሞት ፡ ብዙ ፡ ምክንያት ፡ አለ
ውና ።

፩፻፶ በደስ ፡ ፅ፳ ፡ በጊዜው ፡ ሁሉ ፡ የነቃን ፡ መሆን ፡
ይገባናል ። የእግዚአብሔርን ፡ ቦታ ፡ እስከና
ገኝ ፡ ድረስ ፡ ለዓይናችን ፡ መኝታ ፡ ለቅንድባ
ችን ፡ እንቅልፍ ፡ እንስጥ ፡ አንዱስ ፡ እንኳ ፡

ወኢይበል ፡ ፩ዱሂ ፡ አነ ፡ ተጠመቁ ፡ ጥምቀተ ፡
ክርስትና ፡ ወነሣእኩ ፡ ሥጋሁ ፡ ለክርስቶስ ፡
ወተአመንኩ ፡ ወኢየሐሊ ። ወኢይበል ፡ ክርስ
ቲያናዊ ፡ አነ ፡ እንዘ ፡ ለሊሁ ፡ ያፈቅር ፡ ኃጢአ ፡
ወኢይትመየጥ ፡ ኀበ ፡ ግቢረ ፡ ትእዛዛቲሁ ፡ ለክርስ
ቶስ ፡ ወይከውን ፡ በአምሳለ ፡ ፩ዱ ፡ ዘቦአ ፡
ውስተ ፡ ቤተ ፡ ምሕፃብ ፡ ወውእቱ ፡ እንዘ ፡
ምሉእ ፡ ርስሐተ ። ወለእመ ፡ ወፅአ ፡ እንዘ ፡
ኢይትሐፀብ ፡ ወኢያጸሪ ፡ ርስሐቶ ፡ ምዕረ ፡
ወይዌስክ ፡ ርስሐተ ፡ በዲበ ፡ ርስሐቱ ፡ ወካዕበ ፡
ይከውን ፡ ስላቀ ፡ ሰዲያብሎስ ፡ እስመ ፡ እሙ
ንቱ ፡ ብህልዎ ፡ በአፉሆሙ ፡ ቀዳሚ ፡ ንሕነ ፡
ንክሕደከ ፡ አ ፡ ዲያብሎስ ፡ ወይእዜሰ ፡ እሙ
ንቱ ፡ ያፈጥኑ ፡ ሐዊረ ፡ ኀበ ፡ ግቢረ ፡ ምግባሩ ፡
እኩይ ።

፩፻፶፭ ወእመቦ ፡ ዘይብል ፡ በእንተ ፡ ርእሱ ፡ አነ ፡ ክር
ስቲያናዊ ፡ ወኢኮነ ፡ ውእቱ ፡ ለባሴ ፡ ምግባር ፡
እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይሰመይ ፡ በኀበ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ወበኀበ ፡ ሰብእ ፡ ሰይጣነ ፡ በእንተ ፡ ዘኢ
ጸልአ ፡ ግብረ ፡ ሰይጣን ፡ እላ ፡ ጸንዐ ፡ ቦቱ ፡ በእ
ንተ ፡ ዝንቱ ፡ ይሰመይ ፡ በስሞሙ ፡ ለሰይጣ
ናት ፡ በዝየ ፡ ወበድኅረ ፡ ይከውን ፡ መክፈል
ቶሙ ፡ ሶበ ፡ ሞተ ፡ በዝንቱ ፡ ምግባር ፡ ርኩስ ።

፩፻፶፮ ዶቅ ፡ ፫ቱ ፡ ለክርስቲያናዊ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡
ይኩን ፡ ሑረቱ ፡ በትእዛዘ ፡ ክርስቶስ ፡ ወይት
መሰሎ ፡ በኵሉ ፡ ግብሩ ፡ ወኢያኩን ፡ ጽልሕወ ፡
ወኢፈታዌ ፡ ለዘይትሐጐል ፡ ግብር ፡ ወኢይ
ዝሩ ፡ ንዋዮ ፡ ኀበ ፡ ዘአልቦ ፡ ውስቴቱ ፡ መድ
ኃኒት ፡ ወኢይኩን ፡ ተገባሬ ፡ ዘኢይደሉ ፡ ወኢ
ውኑደ ፡ ምሕረት ፡ ወኢመፍቀሬ ፡ አንስት ፡
ዳእሙ ፡ ያውስብ ፡ አሐተ ፡ ብእሲተ ፡ ወይሕ
ፅን ፡ ውሉዶ ፡ በፈሪሀ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢይ
ኅየይ ፡ እመከራት ፡ ወያንብብ ፡ ወይሰቡ ፡ ዘይ
ሰምዖ ፡ ወየሀብ ፡ እምዘሎቱ ፡ ፍጡነ ። ወኢይ
ኩን ፡ ሀካየ ፡ ወኢይመንን ፡ እግ ብርቲሁ ፡ እላ ፡
ይኅልቆሙ ፡ በአምሳለ ፡ ውሉዱ ። ወኢይኩን ፡
ጽኑዐ ፡ በነሢእ ፡ ወውሂብ ፡ ወኢይትሀከይ ፡
ለውሂበ ፡ መባእ ፡ በእንተ ፡ ቍርባን ፡ ወዕጣን ።
ወለእመ ፡ ኮነ ፡ መሢሐዊ ፡ ጽኑዐ ፡ በዝንቱ ፡
ኵሉ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ዘተመሰሎ ፡ ለክርስ
ቶስ ፡ ወውእቱ ፡ ይሄሉ ፡ በየማኑ ፡ ወይሴብሕ ፡
ምስለ ፡ መላእክት ፡ ወያነሥእ ፡ እምኀቤሁ ፡
አክሊለ ፡ ሕይወት ፡ ዘአስተፈሥሖሙ ፡ ለፍቁራ
ኒሁ ።



እኔ ፡ የክርስትናን ፡ ጥምቀት ፡ ተጠምቄያለሁ ፡
አይበል ፡ የክርስቶስን ፡ ሥጋና ፡ ደም ፡ ተቀብ
ያለሁ ፡ እምኛለሁም ፡ አይበል ፡ አያስብ ፡ እርሱ ፡
ጠብን ፡ እየወደደ ፡ የክርስቶስንም ፡ ትእዛዞች ፡
ወደ ፡ መሥራት ፡ ሳይመለስ ፡ እኔ ፡ ክርስቲያናዊ
ነኝ ፡ አይበል ፡ ወደመታጠብያ ፡ ቤት ፡ በገባ ፡
በአንዱ ፡ አምሳል ፡ ይሆናል ፡ እርሱም ፡ እድ
ፋን ፡ የተመላ ፡ ነው ። ሳይታጠብ ፡ ቢወጣ ፡
አንድ ፡ ጊዜ ፡ አድፉን ፡ ባያጠራ ፡ በአድፉ ፡
ላይ ፡ አድፍን ፡ ይጨምራል ። ዳግመኛም ፡ የዲ
ያብሎስ ፡ መዘባበቻ ፡ ይሆናል ፡ እነርሱ ፡ በአፋ
ቸው ፡ በመጀመሪያ ፡ ዲያብሎስ ፡ ሆይ ፡ እኛ ፡
እንክድሃለን ፡ ብለውታልና ፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ እነ
ርሱ ፡ ክፉ ፡ ሥራውን ፡ ወደመሥራት ፡ ሰመ
ሄድ ፡ ይፋጠናሉ ።

፩፻፶፭ በራሱ ፡ እኔ ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ነኝ ፡ የሚል ፡ ቢኖ
ር ፡ እርሱ ፡ ክርስቲያናዊ ፡ አይደለም ። የሰይጣ
ንን ፡ ሥራ ፡ ስላልጠላ ፡ በሰውና ፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ ዘንድ ፡ ሰይጣን ፡ ይባላልና ፡ ኖረበት ፡
እንጂ ፡ ስለዚህ ፡ ዛሬም ፡ በኋላም ፡ በሰይጣናት ፡
ስም ፡ ይጠራል ፡ በዚህ ፡ በረከሰ ፡ ሥራ ፡ በሞተ
ጊዜ ፡ ድርሻቸው ፡ ይሆናል ።

፩፻፶፮ ዶቅ ፡ ፫ ፡ ለክርስቲያናዊ ፡ ሰው ፡ አኗኗሩ ፡ በክር
ስቶስ ፡ ትእዛዝ ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ።
በሥራው ፡ ሁሉ ፡ ይምሰለው ፡ ከዳተኛ ፡ የሚጠ
ፋውን ፡ የሚወድ ፡ አይሁን ። መድን ፡ በሌለ
በት ፡ ቦታ ፡ ገንዘቡን ፡ አይበትን ፡ የማይገባውን
የሚሠራ ፡ ይቅርታ ፡ የጐደለው ፡ ሴት ፡ ወዳጅ ፡
አይሁን ፡ አንዲት ፡ ሚስት ፡ ያግባ ፡ እንጂ ፡
ልጆቹንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመፍራት ፡ ያሳ
ድግ ፡ በመከራ ፡ ጊዜ ፡ አይክዳ ፡ ያንብብ ፡ የሚ
ሰማውን ፡ ያስተውል ፡ ካለው ፡ ፈጥኖ ፡ ይስጥ ፡
ጨካኝ ፡ አይሁን ፡ በልጆቹ ፡ አምሳል ፡ ይቁጠ
ራቸው ፡ እንጂ ፡ አገልጋዮቹን ፡ አይናቅ ፡ በመ
ቀበልና ፡ በመስጠት ፡ የፀና ፡ አይሁን ፡ የቍር
ባንና ፡ የዕጣን ፡ መባዕ ፡ ለመስጠት ፡ ቸል ፡
አይበል ። ክርስቲያናዊ ፡ በዚህ ፡ ሁሉ ፡ የፀና ፡
ቢሆን ፡ ክርስቶስን ፡ የሚመስለው ፡ እርሱ ፡
ነው ፡ በቀኙ ፡ ይቀመጣል ፡ ከመላእክትም ፡ ጋር
ያመሰግናል ፡ ለወዳጆቹ ፡ ተስፋ ፡ ያደረገላ
ቸውን ፡ የሕይወት ፡ አክሊል ፡ ከርሱ ፡ ዘንድ ፡
ይቀበላል ።

### እንቀጽ ፡ ፲፩ ።

፩፻፶፫ ኢታፍቅሩ ፡ ብሩረ ፡ አ ፡ መፍቀርያነ ፡ እግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ ሥርወ ፡ እከያት ፡ ውእቱ ፡ አፍቅሮ ፡ ንዋይ ፡ የአከለነ ፡ ረኪበ ፡ መብልዕ ፡ ወልብስ ፤ ወናሁ ፡ ተጽሕፈ ፡ በእንቲአነ ፡ ዘይብል ፡ "ግድፍ ፡ ላዕለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕሊናከ ፡ ወውእቱ ፡ ይሴስየከ" ።

፩፻፶፬ ድስቅ ፡ ፳ወ፪ቱ ፡ ኩኑ ፡ ድልዋነ ፡ ከመ ፡ ታፍዋኑ ፡ ሐዊረ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በኵሉ ፡ ትጋህ ፡ ዘእንበለ ፡ ሀኬት ፤ ወኢትኅድጉ ፡ ግብረ ፡ እደዊክሙ ፡ ከመ ፡ ትኩኑ ፡ ኩሎ ፡ መዋዕሊክሙ ፡ ከመ ፡ ትርከቡ ፡ ዘትሴሰዩ ፡ ቦቱ ፡ አንትሙ ፡ ወነዳያን ።

፩፻፶፭ ክፍል ፡ ዳግም ፡ ወውእቱ ፡ ላዕለ ፡ ፫ቱ ፡ ጾታ ። ቀዳማዊ ፡ በእንተ ፡ ዘይደልዎሙ ፡ ለአበው ፡ ይግበሩ ፡ ላዕለ ፡ ውሉዶሙ ፡ ወውሉድኒ ፡ ለአበዊሆሙ ፡ ሥጋውያን ። ድስቅ ፡ ፳ወ፪ቱ ፡ አ ፡ እበው ፡ መሀርዎሙ ፡ ለውሉድክሙ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወሕፅንዎሙ ፡ በተግሣጽ ፡ ወአእምሮተ ፡ እግዚአብሔር ። ወመሀርዎሙ ፡ ኪናተ ፡ ዘይደልዎሙ ፡ ከመ ፡ ኢያስተሐምሙ ፡ ለግብረ ፡ ዕርዐት ፤ ወኢየሐልዩ ፡ ፍጹመ ፡ ውስተ ፡ ገዲፈ ፡ ወላድያኒሆሙ ፡ ወሐፃንያቲሆሙ ። ወለእመ ፡ ኀደግዎሙ ፡ ወኢገሠጽዎሙ ፡ ወነበሩ ፡ ውስተ ፡ ዕረፍት ፡ እምቅድመ ፡ ጊዜ ፡ ይከውኑ ፡ ጽኑዓነ ፡ ወይትገነሡ ፡ እምሠናያት ፤ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ኢትፍርሁ ፡ እምገሥጾቶሙ ፡ ወምሂሮቶሙ ፡ በአፍርሆ ። እስመ ፡ አንትሙ ፡ ኢትቀትልዎሙ ፡ ሶበ ፡ መሀርክምዎሙ ፤ አላ ፡ ታሐይውዎሙ ፤ በከመ ፡ ይቤ ፡ ሰሎሞን ፡ በጥበቡ ፡ "ገሥጾ ፡ ለወልድከ ፡ ከመ ፡ ያዕርፍከ ፡ ወይርባኅከ ። እስመ ፡ ውእቱ ፡ ተስፋከ ፡ ሠናይ ፤ ወሶበ ፡ ዘበጥኮ ፡ በበትር ፡ ነፍሶ ፡ ታሐዩ ፡ እሞት ።

፩፻፶፮ ወመሀርዎሙ ፡ ለውሉድክሙ ፡ ነገረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወከልልዎሙ ፡ በዝብጠት ፡ ከመ ፡ ይትአዘዙ ፡ ለክሙ ፡ እምንእሶሙ ። ወመሀርዎሙ ፡ ኵሎ ፡ መጻሕፍተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢታዕርፍዎሙ ፡ ከመ ፡ ኢይትኀየሉ ፡ ላዕሌክሙ ፡ ወኢይዓኡ ፡ እምትእዛዛቲክሙ ፡ ወኢትኅድግዎሙ ፡ ይሑሩ ፡ ኀበ ፡ ሰቴ ፡ ምስለ ፡ እብያጺሆሙ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ይትመየጡ ፡ ኀበ ፡ እከያት ። ወሶበ ፡ አበሱ ፡ በሀኬተ ፡ እበዊሆሙ ፡ እኮ ፡ እሙንቱ ፡ ባሕቲቶሙ ፡ ዘይትኬነኑ ፡

### ስለ ፡ ሕዝባውያን ፡ ተግሣጽ ።

፩፻፶፫ የእግዚአብሔር ፡ ወዳጆች ፡ ሆይ ! ብር ፡ አትውደዱ ፡ የኃጢአት ፡ ምንጭ ፡ ገንዘብ ፡ መውደድ ፡ ነውና ፡ ምግብ ፤ ልብስ ፡ ካገኘን ፡ ይበቃናል ፤ "አሳብህን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ጣል ፡ እርሱ ፡ ይመግብሃል ፡ የሚል ፡ እነሆ ፡ ተጽፏል" (መዝ ፡ ፶፬ ፡ ፳፪) ።

፩፻፶፬ ድስቅ ፡ ፳፪ ፡ ያለ ፡ ስንፍና ፡ በፍጹም ፡ ትጋት ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለመሄድ ፡ ትፋጠኑ ፡ ዘንድ ፡ የተዘጋጃችሁ ፡ ሁኑ ። የእጃችሁንም ፡ ሥራ ፡ አትተዉ ፡ በዘመናችሁ ፡ ሁሉ ፡ እናንተና ፡ ነዳያን ፡ የምትመገቡትን ፡ ታገኙ ፡ ዘንድ ።

፩፻፶፭ ፪ኛው ፡ ክፍል ፡ ይኸውም ፡ ፫ት ፡ ወገን ፡ ነው ፡ መጀመሪያው ፡ አባቶች ፡ ለልጆቻቸው ፡ ልጆችም ፡ ለአባቶቻቸው ፡ ሊያደርጉላቸው ፡ ስለሚገባቸው ፡ ይናገራል ። ድስቅ ፡ ፳፪ ፡ አባቶች ፡ ሆይ ፡ ልጆቻችሁን ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ አስተምሯቸው ። እግዚአብሔርን ፡ በማወቅ ፤ በምክር ፡ አሳድጓቸው ፤ ሥራ ፡ ፈት ፡ እንዳይሆኑ ፡ የሚገባቸውን ፡ ጥበብ ፡ አስተምሯቸው ፤ ወላጆቻቸውንና ፡ ሞግዚቶቻቸውን ፡ እንረዳም ፡ ብለው ፡ በፍጹም ፡ እንዳያስቡ ። ቢተዋቸው ፡ ባይቀጧቸው ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ከማድረሳቸው ፡ በፊት ፡ በሥራ ፡ ፈት ፡ ቢኖሩ ፡ በክፉ ፡ ሥራ ፡ የፀኑ ፡ ይሆናሉ ። ከበጎ ፡ ነገርም ፡ ይርቃሉ ፤ ስለዚህ ፡ በማስፈራራት ፡ ከመቆጣትና ፡ ከማስተማር ፡ አትፍሯቸው ፡ ባስተማራችኋቸው ፡ ጊዜ ፡ ታድኗቸዋላችሁ ፡ እንጂ ፡ አትገድሏቸውምና ። ሰሎሞን ፡ በመጽሐፉ ፡ "ልጅህን ፡ ቅጣው ፡ ዕረፍት ፡ ይሰጥህ ፡ ዘንድ ፡ ይጠቅምህም ፡ ዘንድ ፡ በጎ ፡ እለኝታህ ፡ እርሱ ፡ ነውና ፡ በበትር ፡ በመታኸው ፡ ጊዜ ፡ ሰውነቱን ፡ ከሞት ፡ ታድናለህ" እንዳለ ። (ምሳሌ ፡ ፳፫ ፡ ፲፫-፲፬)

፩፻፶፮ ልጆቻችሁን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ አስተምሯቸው ፡ ከትንሽነታቸው ፡ ጀምረው ፡ ይታዘዙላችሁ ፡ ዘንድ ፡ በበትር ፡ ጋርዱዋቸው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መጻሕፍት ፡ ሁሉ ፡ አስተምሯቸው ፡ እንዳይበረታቱባችሁ ፡ ከትእዛዛችሁ ፡ እንዳይወጡ ፡ አታሳርፏቸው ፡ ከባልንጀሮቻቸው ፡ ጋር ፡ ወደመጠጥ ፡ ይሄዱ ፡ ዘንድ ፡ አትተዋቸው ፡ ስለዚህ ፡ ወደክፋት ፡ ይመለሳሉ ። በአባቶቻቸው ፡ ስንፍና ፡ ቢበድሉ ፡ እነርሱ ፡ ብቻ ፡ የሚቀጡ ፡ አይደለም ፡ ስለእነርሱ ፡

ዳእሙ ፡ እበዊሆሙኒ ፡ ይትኴነኑ ፡ በእንቲአሆሙ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ገሥጽዎሙ ፡ ወበ ጊዜ ፡ ዘይደሉ ፡ ሎሙ ፡ እውሰቦ ፡ እስተዋስብዎሙ ፡ እንስተ ፡ ንጹሐተ" ። ወጳውሎስኒ ፡ ይብል ፡ ኢርቱዕ ፡ ደቂቅ ፡ ይዝግቡ ፡ መዝገበ ፡ ለእበዊሆሙ ፡ እላ ፡ እበው ፡ ለውሉዶሙ ።

፩፻፶፯ ዘኤፌሶን ፡ ፮ቱ ፡ "አ ፡ ውሉድ ፡ ተእዘዙ ፡ ለእበዊክሙ ፡ ከመ ፡ ዘለእግዚእን ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ምግባረ ፡ ጽድቅ" ፡ ወትእዛዝኒ ፡ ቀዳማዊ ፡ ይቤ ፡ "አክብር ፡ እባከ ፡ ወእመከ ፡ ከመ፡ ሠናየ ፡ ይኩንከ ፡ ወይኑኅ ፡ መዋዕሊከ ፡ በምድር ። አ ፡ እበው ፡ ኢታስተቀጥዑ ፡ ውሉደከሙ ፡ እላ ፡ እልህቅዎሙ ፡ በተግሣጽ ፡ ሠናይ ፡ ወበትምህርተ ፡ እግዚእነ" ።

፩፻፶፰ ሥርዋጽ ፡ ፲ቱ ፡ ነበረ ፡ ውስተ ፡ ቀኖናት ፡ ዘነገሥት ፡ ወድልው ፡ ለእግዚእብሔር ፡ ሳዕለ ፡ በኵር ፡ ዘይትወለድ ፡ ዐቂበ ፡ እቡሁ ፡ ወሀቂበ ፡ እኃዊሁ ፡ እምድኅረ ፡ እቡሆሙ ፡ ወለእግዚእብሔር ፡ ሳዕለ ፡ እለ ፡ ይፈቅዱ ፡ ከመ ፡ ያእምሩ ፡ ጽድቆ ፡ ወይዐመዱ ፡ ለተእዝዞቱ ፡ ወከማሁ ፡ ይደሉ ፡ ሳዕለ ፡ ኵሉ፦ ሊቅ ፡ ዘይሠየም ፡ እምድኅረ ፡ ቢጹ ።

፩፻፶፱ ቈላስይስ ፡ ፫ቱ ፡ አ ፡ ውሉድ ፡ ተእዘዙ ፡ ለእበዊክሙ ፡ በኵሉ ፡ ግብር ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ሠናይ ፡ በኀበ ፡ እግዚእን ። አ ፡ እበው ፡ ኢታስተቀጥዕዎሙ ፡ ለውሉድክሙ ፡ በከንቱ ፡ ከመ ፡ ኢይኅዝኑ ። በሰ ፡ ፳ወ፰ቱ ፡ መሀርዎሙ ፡ ለውሉድክሙ ፡ ከመ ፡ ይጸልዩ ፡ ጸሎተ ፡ ሰዓታት ፡ ኅቡሉ ፡ ንጽሕ ። ድስቅ ፡ ዘ፱ቱ ፡ ወአክብር ፡ እባከ ፡ ወእመከ ፡ ሥጋውያነ ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ምክንያተ ፡ ልደትከ ።

፩፻፷ ወዳግምኒ ፡ ጾታ ፡ በእንተ ፡ እፍቅሮተ ፡ እደው ፡ ለእንስቲያሆሙ ፡ ወተእገዞተ ፡ እንስትኒ ፡ ለእምታቲሆን ። ወይቤ ፡ ጳውሎስ ፡ በመልእክቱ ፡ ለሰብእ ፡ ኤፌሶን ፡ ፭ቱ ። "ወእንስትኒ ፡ ይግርሩ ፡ ለእምታቲሆን ፡ በከመ ፡ ይገርሩ ፡ ለእግዚእብሔር ፡ እስመ ፡ ብእሲ ፡ ርእሳ ፡ ለብእሲት ፡ ውእቱ ። ወይደልዎሙ ፡ ለእደው ፡ ከመ ፡ ያፍቅሩ ፡ እንስተ፡ያሆሙ ፡ ከመ ፡ እፍቅሮተ ፡ ሥጋሆሙ ፡ ወኵሉ ፡ ለለ፩ዱ ፡ እምኔክሙ ፡ ያፍቅር ፡ ብእሲቶ ፡ ከመ ፡ ነፍሱ ። ወከማሁ ፡ ብእሲትኒ ፡



አባቶቻቸውም ፡ ይቀጣሉ ፡ እንጂ ፡ ስለዚህ ፡ ገሥጹቸው ፡ ማግባት ፡ በሚገባቸውም ፡ ጊዜ ፡ ንጹሕ ፡ የሆኑትን ፡ ሴቶች ፡ አጋቢቸው ። ጳውሎስም ፡ "ልጆች ፡ ለወላጆቻቸው ፡ ድልብን ፡ ማድለብ ፡ አይገባቸውም ፡ አባቶች ፡ ለልጆቻቸው ፡ ነው ፡ እንጂ" (፪ኛ ፡ ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፲፬) ፡ አለ ።

፩፻፶፯ ኤፌሶን ፡ ፮ ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፡ ለጌታችን ፡ እንደምትታዘዙ ፡ ለአባቶቻችሁ ፡ ታዘዙ ፡ ይህ ፡ የእውነት ፡ ሥራ ፡ ነውና ፡ መጀመሪያውም ፡ ትእዛዝ ፡ እባትህንና ፡ እናትህን ፡ አክብር ፡ በጎ ፡ ይደረግልሀ ፡ ዘንድ ፡ በምድርም ፡ ዕድሜህ ፡ ይረዝም ፡ ዘንድ ፡ አለ ። አባቶች ፡ ሆይ ፡ ልጆቻችሁን ፡ አታበሳጩ ፡ በበጎ ፡ ምክር ፡ በጌታችን ፡ ትምህርት ፡ አሳድጓቸው ፡ እንጂ ። (ኤፌሶን ፡ ፮ ፡ ፩ - ፬) ።

፩፻፶፰ ሥርዋጽ ፡ ፲ ፡ በነገሥታት ፡ ሕግ ፡ ተጻፈ ፡ ከወላጆቹ ፡ በኋላ ፡ አባቱንና ፡ ወንድሞቹን ፡ ለመርዳት ፡ በኵር ፡ ሁኖ ፡ የተወለደው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተገባ ፡ ነው ። የእግዚአብሔርንም ፡ ቸርነት ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ በወደዱት ፡ ለትእዛዙ ፡ ይገዙ ፡ እንደዚሁም ፡ ከባልንጀራው ፡ ቀጥሎ ፡ ለሚሾም ፡ አለቃ ፡ ሁሉ ፡ መታዘዝ ፡ ይገባል ።

፩፻፶፱ ቆላስይስ ፡ ፫ ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፡ በሥራው ፡ ሁሉ ፡ ለአባቶቻችሁ ፡ ታዘዙ ፡ ይህ ፡ በጌታችን ፡ ዘንድ ፡ በጎ ፡ ነውና ፡ አባቶች ፡ ሆይ ፡ በከንቱ ፡ እንዳያዝኑ ፡ ልጆቻችሁን ፡ አታበሳጭዋቸው ። (ቆላስይስ ፡ ፫ ፡ ፳ - ፳፩) ። በሰ ፡ ፳፰ ፡ በፍጹም ፡ ንጽሕና ፡ የሰዓቱን ፡ ጸሎት ፡ ይጸልዩ ፡ ዘንድ ፡ ልጆቻችሁን ፡ አስተምሯቸው ። ድስቅ ፡ ፱ ፡ ሥጋውያን ፡ አባትህንና ፡ እናትህን ፡ አክብር ፡ የመወለድህ ፡ ምክንያት ፡ እነርሱ ፡ ናቸውና ።

፩፻፷ ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ወንዶች ፡ ሚስቶቻቸውን፡ ስለመውደዳቸው ፡ ሴቶችም ፡ ለባሎቻቸው ፡ ስለመታዘዛቸው ፡ ይናገራል ። ጳውሎስ ፡ ለኤፌሶን ፡ ሰዎች ፡ በጻፈው ፡ መልእክቱ ፡ በአምስተኛው ፡ ምእራፍ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ሴቶችም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንደሚገዙ ፡ ለባሎቻቸው ፡ ይገዙ ፡ ወንድ ፡ ለሴት ፡ ገዥዋ ፡ ነውና ። ወንዶችም ፡ ራሳቸውን ፡ እንደሚወዱ ፡ ሚስቶቻቸውን ፡ መውደድ ፡ ይገባቸዋል ። ከእናንተ ፡ ወገን ፡ ሁሉም ፡ ለእያንዳንዱ ፡ እንደ ፡ ራሱ ፡

ታፍቅር ፡ ምታ ፡ ወትፍርሆ” ።

፩፻፷፩ ወይቤ ፡ ጴጥሮስ ፡ በመልእክቱ ፡ ቀዳሚት ፡ ዘ፩ቱ ፡ “ወከማሁ ፡ አንትንኒ ፡ አንስት ፡ ተአዘዛ ፡ ለአምታቲክን ፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ እለ ፡ ይትኤዘዙ ፡ ለቃል ፡ ይርብኅዎሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ቃል ፡ በእንተ ፡ ሠናይ ፡ ግእዝን ፡ ለአንስት ፡ ሶበ ፡ ርእዩ ፡ ንጽሐ ፡ ልብክን ፡ ወተመይጦትክን ፡ ኀበ ፡ ንጽሕ ፡ ወጽድቅ ። ወይኩን ፡ ሥርጋዌክን ፡ ከመዝ ፡ አኮ ፡ በሠርጕ ፡ ኀላፊ ፡ ወበተፀፍሮ ፡ ሥዕርት ፡ ወሕልቀተ ፡ ወርቅ ፡ ወለቢሰ ፡ ልብሰ ክቡር ። አላ ፡ ይሠርገዋ ፡ በሠርጎ ፡ ብእሲ ፡ ኅቡእ ፡ ሠርጕ ፡ ዘበእማን ፡ ዘትሄሉ ፡ በልብ ፡ ትሑት ። ሠርጕ ፡ ዘኢትበሊ ፡ ዘትከውን ፡ በነፍስ ፡ ሰላማዊት ። ሠርጕ ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ዘሀለወት ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ እስከ ፡ ለዝሉፉ ። ወከማሁ ፡ ኮና ፡ ቀዳማውያት ፡ አንስት ፡ ቅዱሳት ፡ እለ ፡ ተወከላ ፡ ላዕለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኮነ ፡ ሥርጋዌሆን ፡ ተአዝዞ ፡ ለአምታቲሆን ፡ በከመ ፡ ሳራ ፡ ትትኤዘዞ ፡ ለአብርሃም ፡ ወእግዚእየ ፡ ትብሎ ። ወአንትንሂ ፡ አዋልዲሃ ፡ በምግባረ ፡ ሠናይ ፡ ኢያደንግፅክን ፡ ምንትኒ ፡ መፍርህ ። ወአንትሙኒ ፡ አ ፡ እደው ፡ ከማሁ ፡ ንበሩ ፡ ምስሌሆን ፡ በልባዌ ፡ ወበንጽሕ ፡ ወአኑዝዎን ፡ ከመ ፡ ንዋየ ፡ ልሕኮት ፡ ድኩም ፡ ወአክብርዎን ፡ እስመ ፡ እማንቱ ፡ ይወርሳ ፡ ሕይወተ፡ ዘለዓለም ፡ ምስሌክሙ” ።

፩፻፷፪ በጥንተ ፡ ዲድስቅልያ ፡ ይቤ ፡ አ ፡ እደው ፡ አግብርተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብእሲኒ ፡ እምኔክሙ ፡ ይፁር ፡ ክበደ ፡ ብእሲቱ ፡ ወኢይኩን ፡ ዕቡየ ፡ ወኢጽልሕወ ፡ አላ ፡ ይኩን ፡ መሓሬ ፡ ወረትዐ ፡ ዘያፈጥን ፡ ለአሥምሮተ ፡ ብእሲቱ ። ወኢይሠርገው ፡ በዘትፈትዎ ፡ ብእሲት ፡ ካልእት ፡ ከመ ፡ ኢትስሐት ፡ በርእየተ ፡ ዚአሁ ።

፩፻፷፫ ዘ፫ቱ ፡ ፍርሂዮ ፡ አ ፡ ብእሲት ፡ ለምትኪ ፡ ወኀፊሪ ፡ እምኔሁ ፡ ወአሥምሪዮ ፡ ለውእቱ ፡ ባሕቲቱ ፡ እምድኅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወትግሂ ፡ ለአዕርፎቱ ፡ ወለተልእኮቱ ። ወብእሲት ፡ ጠባብ ፡ ትገብር ፡ ሠናያተ ፡ ኵሎ ፡ ለምታ ፡ ወታስተሐምም ፡ በግብር ፡ ለአግብርቲሃ ፡ ወእ



ሚስቱን ፡ ይውደድ ፡ እንደዚሁ ፡ ሚስትም ፡ ባሏን ፡ ትውደድ ፡ ትፍራውም ። (ኤፌሶን ፡ ፭ ፡ ፳፪ - ፴፫) ።

፩፻፷፩ ጴጥሮስ ፡ በመጀመሪያይቱ ፡ መልእክት ፡ በ፫ተኛው ፡ ምዕራፍ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ እንደዚሁ ፡ እናንተም ፡ ሴቶች ፡ ለባሎቻችሁ ፡ ተገዙ ። ስለሴቶች ፡ በጎ ፡ ጠባይ ፡ በቃል ፡ የማይታዘዙትን ፡ በቃል ፡ የሚታዘዙት ፡ ይጠቅሟቸው ፡ ዘንድ ፡ የልባችሁን ፡ ቅንነት ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ ወደንጽሕና ፡ ወደ ፡ እውነት ፡ መመለሳችሁን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ጌጣችሁ ፡ እንደዚህ ፡ ይሁን ። በሚያልፈው ፡ ጌጥ ፡ የራስን ፡ ፀጉር ፡ በመሠራት ፡ የወርቅ ፡ ቀለበት ፡ በማድረግ ፡ የከበረ ፡ ልብስ ፡ በመልበስ ፡ አይደለም ፡ የባልን ፡ ውስጣዊ ፡ ልቡና ፡ ደስ ፡ በማሰኘት ፡ ያጊጡ ፡ እንጂ ። በተናቀ ፡ ልብ ፡ በምትኖር ፡ በእውነተኛ ፡ ጌጥ ፡ በሰላማዊ ፡ ሰውነት ፡ በምትገኝ ፡ በማትጠፋ ፡ ጌጥ ፡ ያጊጡ ፡ እንጂ ። ይህችውም ፡እስከ ዘለዓለሙ ፡ ድረስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ያለች ጌጥ ፡ ናት ። ለእግዚአብሔር ፡ የተገዙት ፡ የቀደሙት ፡ ደጋግ ፡ ሴቶችም ፡ እንደዚሁ ፡ ነበሩ ። ጌጣቸው ፡ ለባሎቻቸው ፡ በመታዘዝ ፡ ሆነ ። ሣራ ፡ ለአብርሃም ፡ ትታዘዘው ፡ ጌታዬም ፡ ትለው ፡ እንደነበር ፡ እናንተም ፡ ልጆችዋ ፡ በበጎ ፡ ሥራ ፡ ምንም ፡ የሚያስፈራ ፡ አያስደንግጣችሁ ። እናንተም ፡ ወንዶች ፡ እንደዚሁ ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ በማስተዋል ፡ በንጽሕና ፡ ኑሩ ፡ መንገላታት ፡ እንደማይችል ፡ እንደ ፡ ሸክላ ፡ ዕቃ ፡ ያዟቸው ። አክብሯቸውም ፡ እነርሱ ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ የዘለዓለምን ፡ ሕይወት ፡ ይወርሳሉና ።

፩፻፷፪ በዲድስቅልያ ፡ መጀመሪያ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገልጋዮች ፡ ወንዶች ፡ ሆይ ፡ ከእናንተ ፡ ወገን ፡ ወንድ ፡ የሚስቱን ፡ ችግር ፡ ይሸከም ፡ ትእቢተኛ ፡ ከዳተኛ ፡ አይሁን ፡ ቸር ፡ ቅን ፡ ሚስቱን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ የሚፋጠን ፡ ይሁን ፡ እንጂ ። ሌላይቱ ፡ ሴት ፡ በምትወደው ፡ ጌጥ ፡ አያጊጥ ፡ እርሱን ፡ በማየት ፡ እንዳትስት ።

፩፻፷፫ ፫ ፡ ሚስት ፡ ሆይ ፡ ባልሽን ፡ ፍሪው ፡ ከእርሱ ፡ የተነሣ ፡ እፈሪ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በታች ፡ እርሱን ፡ ብቻ ፡ ደስ ፡ አሰኚው ፡ እርሱን ፡ ለማሳረፍና ፡ ለማገልገል ፡ ትጊ ። ብልህ ፡ ሚስት ፡ ለባሏ ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ ታደርጋለች ፡ ለአገልጋዮቿም ፡ በሥራ ፡ ትተጋለች ፡ እጆቿ ፡ ጥቅም ፡ ላለው ፡

ደዊሃ ፡ ይትቀነይ ፡ ለዘቦቱ ፡ በቅኔት ፡ ወእጸብ ዒሃ ፡ ይጸንዓ ፡ ለፈቲል ፡ ከመ ፡ ትጸጉ ፡ ለጽኑ ሳን ፡ ወትግበር ፡ ላቲ ፡ ወለምታ ፡ ፪ተ ፡ አልባስ፡ ወይእቲ ፡ ሶበ ፡ ተሐውር ፡ ውስተ ፡ ፍኖት ፡ ትት ገለበብ ፡ ርእሳ ፡ በዓጽፋ ፡ ወትትገልበብ ፡ በን ጽሕ ፡ ከመ ፡ ትጸወን ፡ ያእቲ ፡ እምርእየ ፡ ሰብእ ፡ እኩያን ። ወኢትሠርገው ፡ ርእሳ ፡ ወገጸ፡ እስመ ፡ እልቦ ፡ በውስቴታ ፡ ምንትኒ ፡ ግብር ፡ በዘትደነስ ፡ ዘያፈቅድ ፡ ሥርጋዌ ። ወያኩን ፡ ገጸ ፡ ድኑነ ፡ እንዘ ፡ ይኔጽር ፡ ታሕተ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ወይእቲ ፡ ትትገልበብ ፡ ወትረ ።

፩፻፹፬ በይስ ፡ ፲ወ፯ቱ ፡ ወብእሲት ፡ ማዕዝት ፡ ኢትጎ ድግ ፡ ሥዕርታ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ቅሉዐ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢተሀብ ፡ ውሉዳ ፡ ለሐፃንያት ፡ ወኢትትህከይ ፡ እመልእክተ ፡ ቤታ ፡ ወኢትትቃሐው ፡ ምስለ ፡ ምታ ።

፩፻፹፭ ማልስ ፡ ጾታ ፡ በእንተ ፡ ከመ ፡ ይትአዘዙ ፡ እግ ብርት ፡ ለአጋእዝተሆሙ ፡ ወአጋእዝትኒ ፡ ከመ፡ ያፍቅርዎሙ ፡ ለእግብርቲሆሙ ። ወይቤ ፡ ጳው ሎስ ፡ በውስተ ፡ መልእክቱ ፡ ለሰብአ ፡ ቈላስ ይስ ፡ ፫ቱ ፡ "አ ፡ እግብርት ፡ ተአዘዙ ፡ ለአጋእ ዝቲክሙ ፡ ሥጋውያን ፡ በኵሉ ፡ ግብር ፡ አኮ ፡ በእድልዎ ፡ ሎሙ ፡ ከመ ፡ ይትአኰቱ ፡ በኀበ ፡ ሰብእ ፡ እላ ፡ በልብ ፡ ሰላማዊ ፡ ወበፍርሃተ ፡ እግዚእብሔር ፡ ወኵሎ ፡ ዘትገብሩ ፡ ሎሙ ፡ ግበሩ ፡ በኵሉ ፡ ልብክሙ ፡ ዘከመ ፡ ትገብሩ ፡ ለእግዚእነ ፡ ወአኮ ፡ ከመ ፡ ዘትገብሩ ፡ ለሰብእ ፡ ወእእምሩ ፡ ከመ ፡ እግዚእ ፡ ይፈድየክሙ ፡ በዕ ሴተ ፡ ኵነኔሁ" ። እስመ ፡ አንትሙ ፡ ለእግዚእ ፡ ክርስቶስ ፡ ገበርክሙ ። ወዘኒ ፡ አበሰ ፡ ይትፈ ደይ ፡ በእበሳሁ ፡ ወአልቦ ፡ በሀየ ፡ እድልዎ ፡ ወኢነሚእ ፡ ገጽ ። አ ፡ አጋእዝት ፡ አሠንዩ ፡ ለእግብርቲክሙ ፡ ወአስተዐርዩ ፡ ማእከሌ ሆሙ ።

፩፻፹፮ ዘኤፌሶን ፡ ፮ቱ ፡ ወኵኑ ፡ ዘተኀድጉ ፡ ሎሙ ፡ አበሳሆሙ ፡ እስመ ፡ አንትሙ ፡ ተእምሩ ፡ ከመ፡ እግዚእ ፡ ብክሙ ፡ በሰማያት ፡ ወአልቦ ፡ በኀ ቤሁ ፡ እድልዎ ፡ ወኢነሚእ ፡ ገጽ ።

፩፻፹፯ በይስ ፡ ፴ወ፰ቱ ፡ ወመኑሂ ፡ ሐዊስ ፡ ኢይሜንን ፡ እግብርቲሁ ፡ እላ ፡ ይኌልቆሙ ፡ ምስለ ፡ ውሉዱ ፡ ወናሁ ፡ ተጽሕፈ ፡ በእንቀጸ ፡ ሰንበት፡ ወበበዓላት ፡ ከመ ፡ ያዕርፉ ፡ ቦሙ ።



ነገር ፡ ይገዛሉ ፡ ለተቸገሩት ፡ ትሰጥ ፡ ዘንድ ፡ ጣቶቿ ፡ ለመፍተል ፡ ይጠንክራሉ ፡ ለእርሷና ፡ ለባሏም ፡ ሁለት ፡ ልብስ ፡ ታበጅ ፡ ዘንድ ፡ ይሀ ችውም ፡ መንገድ ፡ በሄደች ፡ ጊዜ ፡ በልብሷ ፡ ራሷን ፡ ትከናነብ ፡ ክፉዎች ፡ ሰዎችን ፡ ከማ የት ፡ ትጠበቅ ፡ ዘንድ ፡ በንጽሕና ፡ ትሸፈን ። ራሷንና ፡ ፊቷን ፡ አትጌጥ ፡ ኃጢአት ፡ በምት ሠራ ፡ ገንዘብ ፡ ጌጥን ፡ የሚሻ ፡ ሥራ ፡ በርሷ ፡ ዘንድ ፡ ምንም ፡ የለምና ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ በመመ ልከት ፡ ፊቷ ፡ ያዘነበለ ፡ ይሁን ፡ እርሷም ፡ ዘወ ትር ፡ ትከናነብ ።

፩፻፹፬ በይስ ፡ ፲፯ ፡ ነፃ ፡ የሆነች ፡ ሴት ፡ በቤተ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ውስጥ ፡ የተገለጠ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ራሷን ፡ አትተው ። ልጆቿን ፡ ለምግዚት ፡ አት ስጥ ፡ ለቤቷ ፡ ከመሥራት ፡ ቸል ፡ አትበል ፡ ከባሏ ፡ ጋርም ፡ አትጣላ ።

፩፻፹፭ ባሮች ፡ ለጌቶቻቸው ፡ ይታዘዙ ፡ ዘንድ ፡ ጌቶ ችም ፡ ባሮቻቸውን ፡ ይወዱቸው ፡ ዘንድ ፡ ይና ገራል ። ጳውሎስ ፡ ለቈላስይስ ፡ ሰዎች ፡ በጻ ፈው ፡ መልእክቱ ፡ በእምስተኛው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ባሮች ፡ ሆይ ፡ ለሥጋ ውያን ፡ ጌቶቻችሁ ፡ በሥራው ፡ ሁሉ ፡ ታዘዙ ። በሰው ፡ ዘንድ ፡ ይመሰገኑ ፡ ዘንድ ፡ በማድላት ፡ አይደለም ፡ በስላማዊ ፡ ልብ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመፍራት ፡ ነው ፡ እንጂ ። የምትሠሩላቸውን ፡ ሁሉ ፡ ለሰው ፡ እንደምትሠሩት ፡ ያይደለ ፡ ለጌ ታችን ፡ እንደምትሠሩ ፡ በፍጹም ፡ ልቡናችሁ ፡ ሥሩላቸው ። በፍርድ ፡ ቀንም ፡ ጌታ ፡ ዋጋች ሁን ፡ እንደሚከፍላችሁ ፡ እወቁ ። እናንተ ፡ ለጌታ ፡ ክርስቶስ ፡ ሠርታችኋልና ። የበደለም ፡ በበደሉ ፡ ይቀጣል ። በዚያ ፡ ፊት ፡ አይቶ ፡ ማዳ ላት ፡ የለም ፡ ጌቶች ፡ ሆይ ፡ ለባሮቻችሁ ፡ መል ካም ፡ አድርጉ ፡ ሁሉንም ፡ አስተካክሏቸው ። (ቆላስ ፡ ፫ ፡ ፳፪ - ፳፭) ። ፬

፩፻፹፮ ኤፌሶን ፡ ፮ ፡ በደላቸውን ፡ ይቅር ፡ የምትሉላ ቸው ፡ ሁኑ ፡ እናንተ ፡ ጌታ ፡ በሰማያት ፡ እንዳ ላችሁ ፡ ታውቃላችሁና ፡ በእርሱም ፡ ዘንድ ፡ ፊት ፡ አይቶ ፡ ማዳላት ፡ የለም ። (ኤፌ. ፮ ፡ ፱) ።

፩፻፹፯ በይስ ፡ ፴፰ ፡ ክርስቲያን ፡ ግን ፡ ባሮቹን ፡ አይ ናቅ ፡ እንደ ፡ ልጆቹ ፡ ይቍጠራቸው ፡ እንጂ ፡ እነሆ ፡ ያሳርፏቸው ፡ ዘንድ ፡ በሰንበትና ፡ በበዐ ላት ፡ እንቀጽ ፡ ተጻፈ ። (ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ፯፻፳፩) ።

፬፻፳፰ ክፍል ፡ ሣልስ ፡ በእንተ ፡ ዘይትኄነኑ ፡ ቦቱ ። ረስጣ ፡ ፳ወ፱ቱ ፡ መሠርይ ፡ ወዘይትፋወል ፡ በናፍሬ ፡ ዕፅው ፡ ወዛጐል ፡ ዲበ ፡ ሐመድ ፡ ወመንቅሔ ፡ ምወት ፡ ወመተርጕመ ፡ አሕላማት ፡ ወመተርጕመ ፡ ፈጠራ ፡ አው ፡ ዘይጤየር ፡ በአዕዋፈ ፡ ሰማይ ፡ ወዘይትበቀብ ፡ ከመ ፡ ኢይትራከብ ፡ ምስለ ፡ ሐንካስ ፡ አው ፡ ምስለ ፡ ዕዉር ፡ ወዘይትፋወል ፡ በነገረ ፡ ሰብእ ። ፳ወ፲ቱ ፡ ወዘሂ ፡ ይተሉ ፡ ልማዶሙ ፡ ለአረማውያን ፡ ወነገረ ፡ መሀይምኖሙ ፡ ለአይሁድ ። አው ፡ ዘየዐብድ ፡ አው ፡ ዘይኔጽር ፡ ኀበ ፡ ተውኔት ፡ ይኅድጉ ፡ ወእመአኮ ፡ ይሰደዱ ።

፬፻፳፱ ዘዐንቀጸ ፡ ፳ወ፫ቱ ፡ ወከማሁ ፡ ዘይትማረይ ፡ ወዘየበውእሙ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡ ለመሠርያን ፡ ወለካህናተ ፡ ሰይጣን ፡ ወለላእካኒሁ ። ረስጣ ፡ ፳ወ፫ቱ ፡ ረቃዪ ፡ ወዘይፈትሕ ፡ ወየአስር ፡ አው ፡ ዘይጼውዕ ፡ አጋንንተ ። በስ ፡ ፴ወ፰ቱ ፡ ወዘይሰምዕ ፡ ነገረ ፡ መሰግላን ፡ ወዘያስተሐይጽ ፡ ጸሐየ ፡ ሶበ ፡ ይሠርቅ ፡ አው ፡ ወርኀ ፡ ወይገብር ፡ ምንተኒ ፡ ምግባራተ ፡ ወዘየአስር ፡ ላዕሌሁ ፡ ክርቢታተ ፡ ወአስማተ ፡ ሰይጣን ፡ አው ፡ ዘይእኅዝ ፡ ሐጺነ ፡ ለስዲደ ፡ ሰይጣናት ፡ አው ፡ ዘይረቂ ፡ አው ፡ ዘየዕሕስ ፡ በእገሪሁ ።

፬፻፴ ሥርዋጽ ፡ ፲ወ፩ዱ ፡ ነበረ ፡ ውስተ ፡ ቀኖናት ፡ እለ ፡ ይስመዩ ፡ ዘሐዋርያት ፡ ውስቴቱ ፡ ላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ ፳ወ፪ቱ ፡ እምትእዛዘ ፡ ጳውሎስ ፡ እመኒ ዜናዊ ፡ አው ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ ፍኖት ፡ እንዘ ፡ ይእኅዙ ፡ አሕዛ ፡ ውስተ ፡ እደዊሆሙ ፡ ወእለ ፡ ይነግሩ ፡ ተአምራተ ፡ ሐሰወ ፡ ወእለ ፡ ይጽሕፉ ፡ አስማተ ፡ መሐላ ፡ ወእለ ፡ ያደምኑ ፡ ገጾሙ ፡ በጊዜ ፡ ምንዳቤያት ፡ እንዘ ፡ ያንጐረጕሩ ፡ ላዕለ ፡ ፍትሐ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዘየኀትም ፡ እደዊሁ ፡ በመርፍእ ።



፬፻፳፰ ሦስተኛው ፡ ክፍል ፡ ስለሚቀጡበት ፡ ይናገራል ። ረስጣ ፡ ፳፱ ፡ በዕንጨት ፡ ፍሬ ፡ በዛጎል ፡ በአመድ ፡ የሚያሟርት ፡ ሙት ፡ የሚያስነሣ ፡ ሕልም ፡ የሚተረጕም ፡ ፊጥር ፡ የሚተረጕም ፡ ወይም ፡ በሰማይ ፡ ዎፍ ፡ የሚያሟርት ፡ ከአንካሳ ፡ ጋር ፡ ወይም ፡ ከዓይነ ፡ ስውር ፡ ጋር ፡ እንዳይገናኝ ፡ የሚጠበቅ ፡ በሰው ፡ ነገር ፡ የሚያሟርት ፡ ጠንቋይ ። ፳፲ ፡ የአረማውያንን ፡ ልማድ ፡ የአይሁድን ፡ ተረት ፡ የሚከተሉ ፡ ወይም ፡ አውቆ ፡ የሚያብድ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ጨዋታ ፡ የሚመለከት ፡ ይተው ፡ ባይተው ፡ ግን ፡ ይለዩ ።

፬፻፳፱ ዕንቈራ ፡ ፳፫ ፡ እንደዚሁም ፡ የሚያሟርት ፡ ሥራይ ፡ አድራጊዎችን ፡ ካህናተ ፡ ጣዖትን ፡ አገልጋዮቹንም ፡ ወደቤቱ ፡ የሚያገባቸው ፡ ይለይ ። ረስጣ ፡ ፳፫ ፡ የሚረቊ ፡ የሚፈቱ ፡ የሚያስር ፡ ወይም ፡ አጋንንት ፡ የሚጠራ ፡ በስ ፡ ፴፰ ፡ የጠንቋዮቹን ፡ ነገር ፡ የሚሰማ ፡ በሐይ ፡ ወይም ፡ ጨረቃ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ የሚያሟርት ፡ ማናቸውንም ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፡ የአጋንንትን ፡ ስም ፡ በክታብ ፡ የሚያስር ፡ ወይም ፡ ሰይጣናትን ፡ ለማባረር ፡ ብረት ፡ የሚይዝ ፡ የሚረቊ ፡ በእግሩ ፡ የሚያሸበሽብ ።

፬፻፴ ሥርዋጽ ፡ ፲፩ ፡ የሐዋርያት ፡ በተባሉ ፡ ቀኖናት ፡ ውስጥ ፡ በዚሁ ፡ ተጨምሮ ፡ ተነግሯል ፡ ከጳውሎስ ፡ ትእዛዝ ፡ በ፳፪ኛው ፡ ወሬኛ ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ በእጃቸው ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ በጎዳና ፡ የሚቀመጡም ፡ ቢሆኑ ፡ የሐሰት ፡ ተአምራት ፡ የሚያወሩ ፡ የመሐላ ፡ አስማት ፡ የሚጽፉ ፡ በመከራ ፡ ጊዜ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፍርድ ፡ እያንጐራጐሩ ፡ ፊታቸውን ፡ የሚያጠቍሩ ፡ እጁንም ፡ በመርፌ ፡ የሚወጋ ፡ ይተው ።

## አንቀጽ ፡ ፲ወ፱ቱ ።

### በእንተ ፡ ቅዳሴ ።

፬፻፴፩ ድስቅ ፡ ፲ወ፱ቱ ፡ ኒቅያ ፡ ፳ወ፩ዱ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይቁሙ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዘድአት ፡ ወንጽሕ ፡ ወበንቅሐት ፡ ዐቢይ ፡ ለሰሚዐ ፡ ነገረ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጸሐቅ ፡ ዐቢይ ፡ ኵሉ ፡ ለለ፩ዱ ፡ በበመዓርጉ ፡ ዘይደልዎ ፡ በአ

## አንቀጽ ፡ ፲፱ ።

### ስለ ፡ ቅዳሴ ፡

፬፻፴፩ ድስቅ ፡ ፲፱ ፡ ኒቅያ ፡ ፳፩ ፡ በፍጹም ፡ ትጋት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ ለመስማት ፡ ሁሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ በሚገባው ፡ በእየመዓርጉ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ በጸጥታ ፡ በንጽሕና ፡ በፍጹም ፡ ንቃት ፡ ሊቆሙ ፡ ይገባል ። በኅማያ

፩፻፳፰ ክፍል ፡ ሣልስ ፡ በእንተ ፡ ዘይትኄነኑ ፡ ቦቱ ። ረስጣ ፡ ፳ወ፬ቱ ፡ መሠርይ ፡ ወዘይትፋወል ፡ በፍሬ ፡ ዕፅው ፡ ወዘጉል ፡ ዲበ ፡ ሐመድ ፡ ወመንቅሔ ፡ ምዉት ፡ ወመተርጕመ ፡ እሕላማት ፡ ወመተርጕመ ፡ ፈጠራ ፡ እው ፡ ዘይጤየር ፡ በአዕዋፈ ፡ ሰማይ ፡ ወዘይትበቀብ ፡ ከመ ፡ ኢይትራከብ ፡ ምስለ ፡ ሐንካስ ፡ እው ፡ ምስለ ፡ ዕዉር ፡ ወዘይትፋወል ፡ በነገረ ፡ ሰብእ ። ፳ወ፫ቱ ፡ ወዘሂ ፡ ይተሉ ፡ ልማዶሙ ፡ ለአረማውያን ፡ ወነገረ ፡ መሀደምቶሙ ፡ ለአይሁድ ። እው ፡ ዘየዐብድ ፡ እው ፡ ዘይኔጽር ፡ ኀበ ፡ ተውኔት ፡ ይኅድጉ ፡ ወእመእኮሰ ፡ ይሰደዱ ።

፩፻፳፱ ዘዕንቆራ ፡ ፳ወ፫ቱ ፡ ወከማሁ ፡ ዘይትማረይ ፡ ወዘያበውእሙ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡ ሰመሠርያን ፡ ወለካህናተ ፡ ሰይጣን ፡ ወለላእካኒሁ ። ረስጣ ፡ ፳ወ፫ቱ ፡ ረቃዪ ፡ ወዘይፈትሕ ፡ ወየአስር ፡ እው ፡ ዘይጼውዕ ፡ አጋንንተ ። በሰ ፡ ፴ወ፳ቱ ፡ ወዘይሰምዕ ፡ ነገረ ፡ መስግላን ፡ ወዘያስተሐይጽ ፡ ጸሐየ ፡ ሶበ ፡ ይሠርቅ ፡ እው ፡ ወርኀ ፡ ወይገብር ፡ ምንተኒ ፡ ምግባራተ ፡ ወዘየአስር ፡ ላዕሌሁ ፡ ዅርበታተ ፡ ወአስማተ ፡ ሰይጣን ፡ እው ፡ ዘይእኅዝ ፡ ሐጺነ ፡ ለሰዲደ ፡ ሰይጣናት ፡ እው ፡ ዘይረቂ ፡ እው ፡ ዘየዐሕስ ፡ በእገሪሁ ።

፩፻፴ ሥርዋጽ ፡ ፲ወ፩ዱ ፡ ነበረ ፡ ውስተ ፡ ቀኖናት ፡ እለ ፡ ይሰመዩ ፡ ዘሐዋርያት ፡ ውስቴቱ ፡ ላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ ፳ወ፪ቱ ፡ እምትእዛዘ ፡ ጳውሎስ ፡ እመኒ ፡ ዜናዊ ፡ እው ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ ፍኖት ፡ እንዘ ፡ ያእኅዙ ፡ እሕዛ ፡ ውስተ ፡ እደዊሆሙ ፡ ወእለ ፡ ይነግሩ ፡ ተአምራተ ፡ ሐሰወ ፡ ወእለ ፡ ይጽሕፉ ፡ አስማተ ፡ መሐላ ፡ ወእለ ፡ ያደምኑ ፡ ገጸሙ ፡ በጊዜ ፡ ምንዳቤያት ፡ እንዘ ፡ ያንጐረጕሩ ፡ ላዕለ ፡ ፍትሐ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዘየኀትም ፡ እደዊሁ ፡ በመርፍእ ።



፩፻፳፰ ሦስተኛው ፡ ክፍል ፡ ስለሚቀጡበት ፡ ያ[illegible]ራል ። ረስጣ ፡ ፳፱ ፡ በዕንጨት ፡ ፍሬ ፡ በዘጉል ፡ በእመድ ፡ የሚያሟርት ፡ ሙት ፡ የሚያስነሣ ፡ ሕልም ፡ የሚተረጕም ፡ ፈጥሮ ፡ የሚተረጕም ፡ ወይም ፡ በሰማይ ፡ ያፍ ፡ የሚያሟርት ፡ ከአንካሳ ፡ ጋር ፡ ወይም ፡ ከዓይነ ፡ ስዉር ፡ ጋር ፡ እንዳይገናኝ ፡ የሚጠበቅ ፡ በሰው ፡ ነገር ፡ የሚያሟርት ፡ ጠንቋይ ። ፳፫ ፡ የአረማውያንን ፡ ልማድ ፡ የአይሁድን ፡ ተረት ፡ የሚከተሉ ፡ ወይም ፡ እውቆ ፡ የሚያብድ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ጨዋታ ፡ የሚመለከት ፡ ይተዉ ፡ ባይተዉ ፡ ግን ፡ ይለዩ ።

፩፻፳፱ ዕንቈራ ፡ ፳፫ ፡ እንደዚሁም ፡ የሚያሟርት ፡ ሥራይ ፡ አድራጊዎችን ፡ ካህናተ ፡ ጣዖትን ፡ አገልጋዮቹንም ፡ ወደቤቱ ፡ የሚያገባቸው ፡ ይለይ ። ረስጣ ፡ ፳፫ ፡ የሚረጭ ፡ የሚፈታ ፡ የሚያስር ፡ ወይም ፡ አጋንንት ፡ የሚጠራ ፡ በሰ ፡ ፴፭ ፡ የጠንቋዮቹን ፡ ነገር ፡ የሚሰማ ፡ በሐይ ፡ ወይም ፡ ጨረቃ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ የሚያሟርት ፡ ማናቸውንም ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፡ የአጋንንትን ፡ ስም ፡ በክታብ ፡ የሚያስር ፡ ወይም ፡ ሰይጣናትን ፡ ለማባረር ፡ ብረት ፡ የሚይዝ ፡ የሚረጭ ፡ በእግሩ ፡ የሚያሽበሽብ ።

፩፻፴ ሥርዋጽ ፡ ፲፩ ፡ የሐዋርያት ፡ በተባሉ ፡ ቀኖናት ፡ ውስጥ ፡ በዚሁ ፡ ተጨምሮ ፡ ተነግሯል ፡ ከጳውሎስ ፡ ትእዛዝ ፡ በ፳፪ኛው ፡ ወሬኛ ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ በእጃቸው ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ በጎዳና ፡ የሚቀመጡም ፡ ቢሆኑ ፡ የሐሰት ፡ ተአምራት ፡ የሚያወሩ ፡ የመሐላ ፡ አስማት ፡ የሚጽፉ ፡ በመከራ ፡ ጊዜ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፍርድ ፡ እያንጐራጐሩ ፡ ፊታቸውን ፡ የሚያጠቁሩ ፡ እጁንም ፡ በመርፌ ፡ የሚወጋ ፡ ይተው ።

## አንቀጽ ፡ ፲ወ፪ቱ ።

በእንተ ፡ ቅዳሴ ።

፩፻፴፩ ድስቅ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ኒቅያ ፡ ፳ወ፩ዱ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይቁሙ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዘድእት ፡ ወንጽሕ ፡ ወበንቅሐት ፡ ዐቢይ ፡ ለሰሚዐ ፡ ነገረ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጸሕቅ ፡ ዐቢይ ፡ ኵሉ ፡ ለለ፩ዱ ፡ በበመዓርጉ ፡ ዘይደልዎ ፡ በአ

## አንቀጽ ፡ ፲፪ ።

ስለ ፡ ቅዳሴ ፡

፩፻፴፩ ድስቅ ፡ ፲፪ ፡ ኒቅያ ፡ ፳፩ ፡ በፍጹም ፡ ትጋት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ ለመስማት ፡ ሁሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ በሚገባው ፡ በእየመዓርጉ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ በጸጥታ ፡ በንጽሕና ፡ በፍጹም ፡ ንቃት ፡ ሊቆሙ ፡ ይገባል ። በጎማያ

ምሳሌ ፡ ስማያውያን ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ በቅድመ ፡ ምሥዋዕ ፡ ከመ ፡ ሥራዕያን ፡ ወእምድኅሬሆሙ፡ ቀሳውስት ፡ ከመ ፡ መምሀራን ፡ ወሊቀ ፡ ዲያቆናት ፡ በነበሁ ፡ ወዲያቆናትኒ ፡ እምድኅረ ፡ ቀሳውስት ፡ ከመ ፡ ላእካን ። ወከሮስ ፡ ሕዝብ ፡ እምድኅሬሆሙ ፡ ወሬዙት ፡ ውስተ ፡ ፩ዱ ፡ መካን ፡ ባሕቲቶሙ ፡ ወለእመ ፡ ሀለው ፡ ሀየ ፡ መካን ፡ ዘያገምርሞሙ ፡ ይቁሙ ፡ ሕፃናት ፡ ምስለ ፡ አበዊሆሙ ፡ ወከማሁ ፡ አንስትኒ ፡ ውስተ ፡ ፩ዱ ፡ መካን ፡ ባሕቲቶን ፡ እለ ፡ ቦን ፡ ምት ፡ እም፩ዱ ፡ ገጽ ፡ ወአዋልድኒ ፡ እም፩ዱ ፡ ገጽ ። ወለእመ ፡ ኢሀለው ፡ መካን ፡ ለአዋልድ ፡ ይቁማ ፡ ድኅረ ፡ አንስት ፡ ወደናግልስ ፡ ወሰበራት ፡ ይቅድማ ፡ እምኵሎን ፡ በተዋምሂ ፡ ወበጸልዮ ።

፩፻፷፪ ግንር ፡ ጽወጺቱ ፡ ወነገሥትስ ፡ ይቁሙ ፡ በውሣጤ ፡ ምሥዋዕ ፡ ምስለ ፡ ሊቃናት ፡ ወሥራዕያን ።

፩፻፷፫ ድስቅ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ወይኩኑ ፡ ዲያቆናት ፡ ዘያስተሐምሙ ፡ ከመ ፡ ይባእ ፡ ለለ፩ዱ ፡ ፩ዱ ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ ዘሥሩዕ ፡ሎቱ ፡ ወየሐውጽዎሙ ፡ ዲያቆናት ፡ ካዕበ ፡ ለሕዝብ ፡ ከመ ፡ ኢይድቅሱ ፡ ወኢይኑሙ ፡ አው ፡ ከመ ፡ ኢይስሐቁ ፡ አው ፡ ከመ ፡ ኢይሳለቁ ፡ አብያጺሆሙ ።

፩፻፷፬ በስ ፡ ፸ወ፪ቱ ፡ ወዘይስሕቅ ፡ በጊዜ ፡ ቅዳሴ ፡ ለእመ ፡ ከነ ፡ ካህን ፡ ይትኃጸብ ፡ ፩ዱ ፡ ሰባዔ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ሕዝባዊ ፡ ይፃእ ፡ በውእቱ ፡ ጊዜ ፡ ወኢይትመጠው ፡ እምቍርባን ።

፩፻፷፭ ዘ፺ወ፮ቱ ፡ ወኢይትናገር ፡ ፩ዱሂ ፡ ማኅሌ ፡ ውስተ ፡ ምሥዋዕ ፡ ካልአ ፡ ነገረ ፡ ዘኢይትፈቀድ ። ወኢበሀውደ ፡ ምሥዋዕኒ ፡ ካዕበ ፡ ወኢይውርቅ ፡ ምራቀ ፡ ፩ዱሂ ፡ ወውእቱ ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ውስተ ፡ ምሥዋዕ ፡ ዘእንበለ ፡ ዕጸበ ፡ ደዌ ።

፩፻፷፮ በደስ ፡ ፲ወ፯ቱ ፡ ወኢይትናገር ፡ መኑሂ ፡ ማሙሬ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እስመ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔርስ ፡ እኩ ፡ ውእቱ ፡ መካነ ፡ ነገር ፡ ዳእሙ ፡ መካነ ፡ ጸሎት ፡ ምስለ ፡ ፍርሃት ። ወዘይትናገር ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይፃእ ፡ ወኢይትመጠው ፡ በውእቱ ፡ ጊዜ ፡ እምሥጢራት ።

፩፻፷፯ በስ ፡ ፺ወ፪ቱ ፡ ወኢይፃእ ፡ ፩ዱሂ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘእንበለ ፡ በማብር ፡ ዕጹብ ፡ እም



ውያን ፡ አምሳል ፡ ሠራተኞች ፡ እንደመሆና ቸው ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ በመንበሩ ፡ ፊት ፡ ቀጥ ሎም ፡ አስተማሪዎች ፡ እንደመሆናቸው ፡ ቀሳውስት ፡ ሊቀ ፡ ዲያቆኑ ፡ በአጠገቡ ፡ ዲያቆናትም ፡ አገልጋዮች ፡ እንደመሆናቸው ፡ ከቀሳውስት ፡ በኋላ ፡ ከእነርሱም ፡ ቀጥሎ ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ይቁሙ ። ቀጥሎም ፡ ሕፃናት ፡ ብቻቻውን ፡ በአንድ ፡ ቦታ ፡ ይቁሙ ፡ ከዚያ ፡ የሚበቃቸው ፡ ቦታ ፡ ካለ ፡ ሕፃናቱ ፡ ከአባቶቻቸው ፡ ጋር ፡ ይቁሙ ። እንደዚሁም ፡ ባል ፡ ያላቸው ፡ ሴቶች ፡ ብቻቸውን ፡ በአንድ ፡ ቦታ ፡ ከአንድ ፡ ፊት ፡ ይቁሙ ፡ ሴቶች ፡ ልጆችም ፡ ከአንድ ፡ ፊት ፡ ይቁሙ ፡ ለሴቶች ፡ ልጆች ፡ ቦታ ፡ ባይኖር ፡ ከሴቶች ፡ በኋላ ፡ ይቁሙ ። ድንግሎቹና ፡ ባልቴቶቹ ፡ ግን ፡ በመቆምም ፡ በመጸለይም ፡ ከሁሉ ፡ ይቅደሙ ።

፩፻፷፪ ግንር ፡ ጽ፺ ፡ ነገሥታቱ ፡ ግን ፡ ከቤተ ፡ መቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ ከሊቃነ ፡ ከቀዳስያን ፡ ጋር ፡ ይቁሙ ።

፩፻፷፫ ድስቅ ፡ ፲፪ ፡ ዲያቆናት ፡ እያንዳንዱ ፡ በተዘዘለት ፡ ቦታ ፡ ይግባ ፡ ዘንድ ፡ የሚያስተናብሩ ፡ ይሁኑ ፡ ዳግመኛም ፡ ዲያቆናቱ ፡ ሕዝቡን ፡ ይጎብኟቸው ፡ እንዳይተኙ ፡ እንዳያንጐላቹ ፡ ወይም ፡ እንዳይስቁ ፡ ወይም ፡ በባልንጀሮቻቸው ፡ እንዳይዘብቱ ።

፩፻፷፬ በስ ፡ ፸፪ ፡ በቅዳሴ ፡ ጊዜ ፡ የሚስቅ ፡ ካህን ፡ ቢሆን ፡ ቅጣቱ ፡ አንድ ፡ ሱባኤ ፡ ነው ፡ ሕዝባዊ ፡ ቢሆን ፡ በዚያው ፡ ጊዜ ፡ ይውጣ ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ አይቀበል ።

፩፻፷፭ ፺፮ ፡ አንዱስ ፡ እንኳ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ የማይወደድ ፡ ሌላ ፡ ነገርን ፡ ፈጽሞ ፡ አይናገር ፡ ሁለተኛም ፡ በመንበሩ ፡ ዙሪያ ፡ ይኸውም ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ ሳለ ፡ ነው ፡ አንዱስ ፡ እንኳ ፡ የሚያስጨንቅ ፡ ደዌ ፡ ሳያገኘው ፡ ምራቁን ፡ አይትፋ ።

፩፻፷፮ በደስ ፡ ፲፯ ፡ ማንም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ፈጽሞ ፡ አይናገር ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ የነገር ፡ ቦታ ፡ አይደለምና ፡ ከፍርሃት ፡ ጋር፡ የጸሎት ፡ ቦታ ፡ ነው ፡ እንጂ ። በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚናገር ፡ ሰው ፡ ይውጣ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ አይቀበል ።

፩፻፷፯ በስ ፡ ፺፪ ፡ ቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ ከተነበበ ፡ በኋላ ፡ በጭንቅ ፡ ሥራ ፡ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ቅዳሴው ፡

ድኅረ ፡ ተነበ ፡ ወንጌል ፡ ቅዱስ ፡ ዘእንበለ ፡ ይትፈጸም ፡ ዕርገተ ፡ ቍርባን ፡ ወበረከተ ፡ ካህን ፡ ወስርሖት ።

፩፻፷፰ ረስጠብ ፡ ፯፡ ፡ ወነሥኡ ፡ ዘይበውእ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወይሰምዕ ፡ መጻሕፍተ ፡ ወኢይቀውም ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ጸሎት ፡ ያደልዎ ፡ ከመ ፡ ይትሌለይ ።

፩፻፷፱ በደስ ፡ ፴ወ፯ቱ ፡ በሰ ፡ ፺ወ፯ቱ ፡ ወአልባስ ፡ ቅዳሴ ፡ እለ ፡ ይቄድሱ ፡ ቦቶን ፡ ይኩና ፡ ፀዓደወ፡ በከመ ፡ ይደሉ ፡ ለካህናት ፡ ወአኮ ፡ ኅብራተ ። ወእግዚእነሂ ፡ ሶበ ፡ ተወለጠ ፡ ኮነ ፡ አልባሲሁ ፡ ፀዓዳ ፡ ከመ ፡ ብርሃን ፡ ወበውእቱ ፡ ኅብረ ፡ አርእየ ፡ መላእክቲሁ ፡ ያስተርእዩ ፡ ለሰብእ ፡ በእንተ ፡ ሠናይት ፡ ወዝንቲ ፡ እርእየ ፡ ዘእዘዘሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ከመ ፡ ይምጽኡ ፡ በውእቱ ፡ ኅበሁ ፡ በዕለተ ፡ ተናገሮሙ ።

፩፻፸ በስ ፡ ለትኩን ፡ ይእቲ ፡ ልብስ ፡ ዘትወርድ ፡ ውስተ ፡ እእጋረ ፡ ካህናት ፡ ወዓዲ ፡ ትኩን ፡ ሳዕለ ፡ መታክፍቲሆሙ ፡ መንዲል ፡ ስፍሕት ። ወአልባስ ፡ ቅዳሴሰ ፡ ይንበሩ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ሳእክ ፡ ዘቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አው ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ ዘመጻሕፍቲሃ ፡ ወኢይንበሩ ፡ በአፍአ ፡ እምኔሃ ። ወኢይሠእን ፡ ፩ዱሂ ፡ እግእነ ፡ በውግጤ ፡ ምሥዋዕ ፡ በከመ ፡ ይቤሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ ለሙሴ ፡ "ፍታሕ ፡ እግእኒከ ፡ እምእገሪከ ፡ እስመ ፡ መካን ፡ ዘእንተ ፡ ትቀውም ፡ ውስቴቱ ፡ ቅዱስ ፡ ውእቱ" ፡ ወከማሁ ፡ ይቤሎ ፡ ካዕበ ፡ ለኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፡ ረድኡ ።

፩፻፸፩ በስ ፡ ፺ወ፯ቱ ፡ ወኢይውጥኑ ፡ ጸሎተ ፡ ቅዳሴ ፡ ዘእንበለ ፡ ይትጋብኡ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ።

፩፻፸፪ ረስጠብ ፡ ፶ወ፱ቱ ፡ ወይዑር ፡ ዲያቆን ፡ ቍርባነ ፡ እስከ ፡ ምሥዋዕ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ውእቱ ፡ ዘይቄድስ ፡ ይቁሙ ፡ ቀሳውስት ፡ በየማኑ ፡ ወበፀጋሙ ፡ በእምሳለ ፡ አርዳኢሁ ።

፩፻፸፫ ዘኒቅያ ፡ ወኢይደልዎ ፡ ለቀሲስ ፡ ከመ ፡ ይቀድስ ፡ ቍርባነ ፡ ዘእንበለ ፡ ዲያቆን ፡ ዘይዜንዎሙ ፡ ለሰብእ ፡ ጸሎተ ። ወይሰብክ ፡ ሎሙ ፡ በፍርሃት ፡ ወክብር ፡ ወይኩን ፡ ዘያስምዖሙ ፡ በዜንዎቱ ።

፩፻፸፬ ድስቅ ፡ ፴ወ፰ቱ ፡ ፳ወ፫ቱ ፡ ዘ፲ወ፱ቱ ፡ ወይሑ

ሳይፈጸም ፡ ቄስ ፡ ሳይባርክ ፡ ሳያሰናብት ፡ እንዲሁ ፡ እንኳ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አይውጣ ።

፩፻፷፰ ረስጠብ ፡ ፯ ፡ ወደቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚገባና ፡ መጻሕፍትን ፡ የሚያዳምጥ ፡ ሁሉ ፡ ጸሎቱ ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ የማይቆም ፡ ከሆነ ፡ መለየት ፡ ይገባዋል ።

፩፻፷፱ በደስ ፡ ፴፯ ፡ በስ ፡ ፺፯ ፡ ለካህናት ፡ እንደሚገባ ፡ የሚቀድሱባቸው ፡ የቅዳሴ ፡ ልብሶች ፡ ነጫጭ ይሁኑ ፡ ዝንጕርጕር ፡ አይደለም ፡ ጌታችንም ፡ በተለወጠ ፡ ጊዜ ፡ ልብሱ ፡ እንደ ፡ ብርሃን ፡ ነጭ ፡ ነው ፡ መላእክትም ፡ ስለ ፡ ደስታ ፡ በዚህ ፡ ቀለም ፡ መልክ ፡ ለሰው ፡ ታዩ ፡ ይኸውም ፡ ልብስ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ወደርሱ ፡ ይመጡ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ በተናገራቸው ፡ ጊዜ ፡ ያዘዛቸው ፡ ነው ።

፩፻፸ በስ ፡ ይህች ፡ ልብስ ፡ እስከ ፡ ካህናት ፡ ተረከዝ ፡ የምትወርድ ፡ ትሁን ፡ ዳግመኛም ፡ ከትከሻቸው ፡ ላይ ፡ ሰፊ ፡ ሳንቃ ፡ (ከልጅ) ፡ ትሁን ፡ የሚቀደስባቸውም ፡ አልባሳት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ አገልጋይ ፡ (ግበዝ) ፡ ቤት ፡ ይቀመጡ ፡ ወይም ፡ መጻሕፍቱ ፡ ባሉበት ፡ በዕቃ ፡ ቤቱ ፡ ይቀመጡ ። ከርሷ ፡ ውጭ ፡ አይቀመጡ ፡ አንዱስ ፡ እንኳ ፡ በመቅደስ ፡ ውስጥ ፡ ጫማ ፡ አይጫማ ። ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ "ጫማህን ፡ ከእግርህ ፡ አውልቅ ፡ እንዳለው ፡ አንተ ፡ የምትቆምበት ፡ ቦታ ፡ ውስጡ ፡ ቅዱስ ፡ ነውና" (ዘፀ ፡ ፫ ፡ ፭) እንደዚሁ ፡ ዳግመኛ ፡ ደቀመዝሙሩን ፡ የነዌ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱን ፡ አለው ። (ኢያሱ ፡ ፭ ፡ ፲፭) ።

፩፻፸፩ በስ ፡ ፺፯ ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ሳይሰበሰቡ ፡ የቅዳሴውን ፡ ጸሎት ፡ አይጀምሩ ።

፩፻፸፪ ረስጠብ ፡ ፶፱ ፡ እስከ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ድረስ ፡ ዲያቆኑ ፡ ኅብስቱን ፡ ይሸከም ፡ የሚቀድሰው ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ ቢሆን ፡ በደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ አምሳል ፡ ቀሳውስቱ ፡ በቀኙና ፡ በግራው ፡ ይቁሙ ።

፩፻፸፫ ኒቅያ ፡ ቄስ ፡ በፍርሃት ፡ በክብር ፡ የሚሰብክላቸውን ፡ ለሰዎችም ፡ ጸሎቱን ፡ የሚነግራቸውን ፡ ዲያቆኑን ፡ ሳይዝ ፡ መቀደስ ፡ አይገባውም ፡ በስብከቱም ፡ የሚያሰማቸው ፡ ይሁን ።

፩፻፸፬ ድስቅ ፡ ፴፰ ፡ ፳፫ ፡ ፲፱ ፡ ቅዳሴውን ፡ በምስጋና

ጥን ፡ ቅዳሴ ፡ በጸሎተ ፡ አኰቴት ፡ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ይበል ፡ ትርጓሜ ፡ ቃለ ፡ መጻሕፍት ፡ ቅዱሳት ፡ ወእምዝ ፡ ይሁር ቀሲስ ፡ ኀበ ስተ ፡ ወጸዋዐ ፡ አኰቴት ፡ ወየአኀዝ ፡ ኤጲስ ቆጶስ ፡ ማዕጠንተ ፡ ወይዑድ ፡ ቤተ ፡ በውደ ፡ ምሥዋዕ ፡ ፫ተ ፡ ጊዜያተ ፡ በእንተ ፡ ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ወየሀብ ፡ ማዕጠንተ ፡ ዕጣን ፡ ለቀሲስ ፡ ከመ ፡ ይዑድ ፡ ባቲ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ።

፩፻፹፮ ወሶበ ፡ ፈጸሙ ፡ ዘምሮ ፡ ለያንብቡ ፡ ዲያቆናት ፡ ክፍላተ ፡ እመልእክታት ፡ ሐዋርያት ፡ ወስብሐታተ ፡ እመዝሙራት ። ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ያንብቡ ፡ ወንጌለ ፡ ቅዱስ ፡ ወኵሎሙ ፡ ሕዝብ ፡ እንዘ ፡ ይቀውሙ ፡ በአርምሞ ፡ ወዘያነብብስ ፡ ይኩን ፡ ቀሲስ ፡ አው ፡ ዲያቆን ።

፩፻፹፯ በስ ፡ ፻ወ፱ቱ ፡ ወሶበ ፡ ፈጸሙ ፡ አንብቦተ ፡ ወንጌል ፡ ለእመ ፡ ሀሎ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ የአኀዝ ፡ በእዴሁ ፡ ወንጌለ ፡ ወይንግሮሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ትርጓሜሁ ፡ በምዕራፋቲሁ ፡ ዘተነበ ። ወለእመ፡ ኢሀሎ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ይግበር ፡ ዘንተ ፡ ቀሲስ ፡ ዘየአምር ፡ ተርጕሞቶ ።

፩፻፹፰ ዘቆርንቶስ ፡ ፲ወ፬ቱ ፡ ወሶበ ፡ ትትናገሩ ፡ ነገረ ፡ በልሳን ፡ ካልእ ፡ ወኢትተረጕምዎ ፡ እፎ ፡ ይትአመር ፡ ዘትብሉ ፡ አንትሙሰ ፡ አሚሃ ፡ ትከውኑ ፡ ከመ ፡ ዘይትናገር ፡ ምስለ ፡ ነፋስ ። ዘ፲ወ፫ቱ ፡ ወይትናገሩ ፡ ለለ፩፩ ፡ ፩፩ ፡ ወይተርጕምሎቱ ፡ ካልእ ፡ ወለእመሰ ፡ ኢሀሎ ፡ ዘይተረጕም ፡ ያርምም ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዝኩ ፡ ዘይትናገር ፡ በልሳን ፡ ካልእ ።

፩፻፹፱ ድስቅ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ወእምድኅረ ፡ ትርጓሜ ፡ ወንጌል ፡ ይጸሊ ፡ ወያስተብቍዕ ፡ በእንተ ፡ ድዉያን ፡ ወነጋድያን ፡ ወምንዱባን ፡ በእንተ ፡ ነፋሳት ፡ ወፍሬያት ፡ ወነገሥት ፡ ወበእንተ ፡ እለ ፡ ኖሙ ፡ ወበእንተ ፡ እለ ፡ ያበውኡ ፡ ቍርባናተ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወእለ ፡ የሐንጽዋ ፡ ወበእንተ ፡ ንኡስ ፡ ክርስቲያን ፡ ወሰላመ ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን ፡ ጉባኤ ፡ ወበእንተ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ወሥዩማን ፡ ካህናት ፡ ወማኅበረ ፡ ሕዝብ ። ወይቀድስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወውእቱ ፡ እንዘ ፡ ቅዉም ፡ ኀበ ፡ ምሥዋዕ ፡ ወመንጦላዕትኒ ፡ እንዘ ፡ ስፉሕት ፡ ወበወማጢሃ ፡ ቀሳውስት ፡ ወዲያቆናት ፡ በውዳ ፡ ወይረውሑ ፡ በመራውሕ ታት ፡ በአምሳለ ፡ አክናፈ ፡ ኪሩቤል ።

፩፻፺ ረስጣ ፡ ፶ወ፪ቱ ፡ ወይቁሙ ፡ ፪ቱ ፡ ዲያቆናት ፡



ጸሎት ፡ ይጀምር ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የትዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ ቃለ ፡ ትርጓሜ ፡ ይበል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቄስ ፡ ንባበስቱንና ፡ የምስጋናውን ፡ ጸዋ ፡ ይያዝ ፡ ኤጲስቆጶስም ፡ ማዕጠንቱን ፡ ይዞ ፡ ስብሐት ፡ ወክብር ፡ ለሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ እያለ ፡ ፫ ጊዜ ፡ ቤተ ፡ መቅደሱን ፡ ይዙር ፡ የዕጣኑን ፡ ማዕጠንት ፡ ለቄስ ፡ ይስጥ ፡ ሕዝቡን ፡ ሁሉ ፡ ያጥንበት ፡ ዘንድ ።

፩፻፹፮ ምስጋናውን ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ ዲያቆናት ፡ ከሐዋርያት ፡ መልእክት ፡ ክፍለው ፡ ያንብቡ ፡ ከመዝሙራትም ፡ ምስጋና ፡ ይስበኩ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቅዱስ ፡ ወንጌልን ፡ ያንብቡ ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ በዝምታ ፡ ቆመው ፡ ሳለ ፡ የሚያነበው ፡ ግን ፡ ቄስ ፡ ወይም ፡ ዲያቆን ፡ ይሁን ።

፩፻፹፯ በስ ፡ ፺፱ ፡ ወንጌሉን ፡ አንብበው ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ ቢኖር ፡ ወንጌሉን ፡ በእጁ ፡ ይዞ ፡ ከተነበበው ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ ትርጓሜውን ፡ ለሕዝቡ ፡ ይንገራቸው ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ ባይኖር ፡ ትርጉሙን ፡ የሚያውቀው ፡ ቄስ ፡ ይስበክ ።

፩፻፹፰ ቆሮንቶስ ፡ ፲፬ ፡ በሌላ ፡ ቋንቋ ፡ ነገርን ፡ ብትነጋገሩ ፡ ባትተረጉሙትም ፡ የምትሉት ፡ እንዴት ፡ ይታወቃል ? እናንተ ፡ ግን ፡ ያንጊዜ ፡ ከነፋስ ፡ ጋር ፡ እንደሚነጋገር ፡ ትሆናላችሁ ። ፲፫ ። እያንዳንዳቸው ፡ በተራ ፡ ይናገሩ ፡ ሌላው ፡ ይተርጕምለት ፡ የ ሚተረጉም ፡ ባይኖር ፡ ግን ፡ በሌላ ፡ ቋንቋ ፡ የሚናገረው ፡ ያ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ዝም ፡ ይበል ።

፩፻፹፱ ድስቅ ፡ ፲፪ ፡ ወንጌል ፡ ከተተረጐመ ፡ በኋላ ፡ ይጸልይ ፡ ስለ ፡ ሕመምተኞቹና ፡ ስለ ፡ መንገደኞቹ ፡ ስለተቸገሩት ፡ ስለ ፡ ነፋሳትና ፡ ስለ ፡ ፍሬዎች ፡ ስለ ፡ ነገሥታት ፡ ስለ ፡ ሞቱት ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መባዕ ፡ ስለሚሰጡትና ፡ ስለ ፡ ሚያንጺት ፡ ስለ ፡ ንዑስ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለ፡እንዲት፡ቤተ፡ ክርስቲያን፡ጸጥታ፡ስለ፡ኤጲስቆጶሳቱና ፡ ስለ ፡ ሹማምቱ ፡ ካህናት ፡ ስለ ፡ ሕዝቡም ፡ አንድነት ፡ ይማልድ ። ኤጲስቆጶሱ ፡ ይኸውም ፡ በመንበሩ ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ መጋረጃውም ፡ ተጋርዶ ፡ ይቀድስ ። በውስጢ ፡ ቀሳውስት ፡ በዙሪያዋ ፡ ዲያቆናት ፡ በኪሩቤል ፡ ክንፍ ፡ አምሳል ፡ በመነሳንስ ፡ ይከልክሉ ።

፩፻፺ ረስጣ ፡ ፶፪ ፡ ሁለት ፡ ዲያቆናት ፡ በመንበሩ ፡

በገበዋተ ፡ ምሥዋዕ ፡ ወየአኀዙ ፡ መራውሕታተ
ዘግቡራት ፡ እምግብር ፡ ልሙጽ ፡ ወይስድዱ ፡
ጽንጽንያተ ፡ ንኡሳነ ፡ ከመ ፡ ኢይደቅ ፡ እምኔ
ሆሙ ፡ ምንትኒ ፡ ውስተ ፡ ጽዋዕ ።

፩፻፺ ድስቅ ፡ ፲ወ፱ቱ ፡ ወዲያቆን ፡ ይቁም ፡ ምስለ ፡
ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ለተልእኮቱ ፡ ወይበል ፡ ለሕ
ዝብ ፡ ዘኢነደገ ፡ መኑሂ ፡ ማእከሌሁ ፡ ወማእ
ከለ ፡ ቢጹ ፡ ጽልሑተ ፡ ወኢእድልዎ ፡ ኢይቅ
ረብ ። ወእምዝ ፡ ይበል ፡ ለለ፩ዱ ፡ እምኔ
እደው ፡ ስዕመተ ፡ ሰላም ፡ ንጽሕተ ፡ ወእምድ
ኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ይትአምኁ ፡ በበይናቲሆሙ ፡
ኵሎሙ ፡ እደው ፡ በአምኃ ፡ ንጽሕት ።

፩፻፺፩ ረስጣ ፡ ፪ወ፫ቱ ፡ ፴ወ፪ቱ ፡ ፶ወ፫ቱ ፡ ወየአምኃ ፡
እንስት ፡ እንስተ ፡ ወኢየአምኁ ፡ እደው ፡ አን
ስተ ፡ ወያምጽእ ፡ ዲያቆን ፡ ማየ ፡ ወይትሐፀቡ ፡
ካህናት ፡ እደዊሆሙ ፡ ወይበል ፡ አለ ፡ ኢትቀ
ርቡ ፡ ፃኡ ።

፩፻፺፪ ድስቅ ፡ ፲ወ፱ቱ ፡ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ያስተብ
ቍዕ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ በእንተ ፡ ሕዝብ ፡ ወይፈ
ጽም ፡ ቅዳሴ ፡ ወኵሎሙ ፡ ሕዝብ ፡ ቅውማኒ
ሆሙ ፡ ይጸልዩ ፡ በህድአት ።

፩፻፺፫ በስ ፡ ፶ወ፱ቱ ፡ ወእለ ፡ ይዜምሩ ፡ በውስተ ፡
ምሥዋዕ ፡ ኢይዘምሩ ፡ በትፍሥሕት ፡ አላ ፡ በል
ባዊ ።

፩፻፺፬ ዘ ፶ወ፱ቱ ፡ ወይክፍል ፡ ሥጋ ፡ በህድአት ፡ በበ
ክፍል ፡ ወይትዐቀብ ፡ ከመ ፡ ኢይደቅ ፡ እም
ኔሁ ፡ ምንትኒ ። ወይክፍል ፡ በዓቅም ፡ ከመ ፡
ኢይኩን ፡ ንኡስ ፡ ወኢዐቢየ ፡ አላ ፡ ምልአ ፡
አፉሁ ፡ ለዘይትሜጦ ፡ ወከመ ፡ ይክዐል ፡
አዑዶቶ ፡ ማእከለ ፡ አፉሁ ። ወይኩን ፡ ለለ፩ዱ ፡
ባሕርየ ፡ ኅብስት ፡ ክፍል ፡ እምኔሁ ፡ ትእምርተ
መስቀል ፡ ቅዱስ ፡ ዲቤሁ ፡ በአምሳለ ፡ መስ
ቀል ፡ ክቡር ፡ ወቅዱስ ።

፩፻፺፭ ዘ ፶ወ፯ቱ ፡ ወሶበ ፡ ተፈጸመት ፡ ጸሎት ፡ ኵለን
ታሃ ፡ ይትአመኑ ፡ ቀሳውስት ፡ በስመ ፡ ሥላሴ ፡
ወይጽርኁ ፡ ኵሎሙ ፡ ሕዝብ ፡ ኅቡረ ፡ ወይ
በሉ ፡ ሕዝብ ፡ አሜን ፡ ነአምን ። ወይበል ፡
ቀሲስ ፡ በአፈ ፡ ዲያቆን ፡ ዘኮነ ፡ ንጹሐ ፡ ይን
ሣእ ፡ እምቍርባን ፡ ወዘኢኮነ ፡ ንጹሐ ፡ ኢይን
ሣእ ፡ እምኔሃ ፡ ከመ ፡ ኢየዐዪ ፡ በእሳተ ፡ መለ
ኮት ። ወዘቦ ፡ ዕቅፍት ፡ ምስለ ፡ ቢጹ ፡ ወዘቦ ፡
ውስቴቱ ፡ ሕሊና ፡ ዝሙት ፡ ወስኪር ፡ ወዘኢ...



አጠገብ ፡ ይቁሙ ፡ ከልዝብ ፡ ሐር ፡ የተሠሩ ፡
መነሳንሶች ፡ ይዘው ፡ ከእነርሱ ፡ ምንም ፡ ወደ ፡
ፅዋው ፡ እንዳይወድቅ ፡ ትናንሾቹን ፡ ዝንቦች ፡
ያባርሩ ።

፩፻፺ ድስቅ ፡ ፲፱ ፡ እርሱን ፡ ለማገልገል ፡ ዲያቆኑ ፡
ከሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ጋር ፡ ይቁም ፡ ለሕዝቡም ፡
እንዲህ ፡ ይበል ፡ በርሱና ፡ በባልንጀራው ፡ መካ
ከል ፡ ቂም ፡ በቀልን ፡ ማዳላትን ፡ ያልተወ ፡
ማንም ፡ አይቍረብ ፡ ይበል ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡
ከወንዶች ፡ ወገን ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ንጹሕ ፡ ሰላ
ምታ ፡ (ተሰጣጡ) ፡ እጅ ፡ ተነሣሡ ፡ ይበል ፡
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወንዶች ፡ ሁሉ ፡ እርስ ፡ በርሳ
ቸው ፡ በንጹሕ ፡ ሰላምታ ፡ እጅ ፡ ይነሣሡ ።

፩፻፺፩ ረስጣ ፡ ፳፫ ፡ ፴፪ ፡ ፶፫ ፡ ሴቶች ፡ ሴቶችን ፡ እጅ ፡
ይንሡ ፤ ወንዶች ፡ ሴቶችን ፡ እጅ ፡ አይንሡ ፡
ዲያቆኑ ፡ ውኃ ፡ ያምጣ ፡ ካህናቱም ፡ እጃቸውን ፡
ይታጠቡ ፡ የማትቆርቡ ፡ ውጡ ፡ ይበል ።

፩፻፺፪ ድስቅ ፡ ፲፱ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ስለ ፡
ሕዝቡ ፡ ይማልድ ፡ ቅዳሴውንም ፡ ይጨርስ ፡
ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ በጸጥታ ፡ ቁመው ፡ ይጸልዩ ።

፩፻፺፫ በስ ፡ ፶፱ ፡ በዚተ ፡ መቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ የሚያ
መሰግኑት ፡ ለቀርእዮ ፡ እያመሰግኑ ፡ ልብ ፡
በማድረግ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡

፩፻፺፬ ፶፱ ፡ በጸጥታ ፡ ሥጋውን ፡ በእየክፍሉ ፡ ይክ
ፈለው ፡ ከርሱ ፡ ምንምን ፡ እንዳይነጥብ ፡ ይጠ
በቅ ፡ ትንሽም ፡ ትልቅም ፡ እንዳይሆን ፡ በልክ
ይክፈለው ፡ በሚቀበለው ፡ ሰው ፡ አፍ ፡ ልክ ፡
ይሁን ፡ እንጂ ። በአፉ ፡ መካከል ፡ ማዘዋወር ፡
ይችል ፡ ዘንድ ፡ እያንዳንዱ ፡ በተከፈለው ፡ ኅብ
ስት ፡ ላይ ፡ ቅዱስ ፡ በሆነው ፡ መስቀል ፡ አም
ሳል ፡ ትእምርተ ፡ መስቀል ፡ ያለበት ፡ ይሁን ።

፩፻፺፭ ፶፯ ፡ ጸሎቱ ፡ ሁሉ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ቀሳው
ስት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ነአምን ፡ ነአምን ፡ ነአምን ፡
ይበሉ ፡ ሕዝቡም ፡ ሁሉ ፡ እየጮኹ ፡ አሜን ፡
እናምናለን ፡ ይበሉ ። ቄሱ ፡ በዲያቆኑ ፡ አፍ ፡
ንጹሕ ፡ የሆነ ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ይቀበል ፡
ይበል ፡ በእሳተ ፡ መለኮት ፡ እንዳይቃጠል ፡
ንጹሕ ፡ ያልሆነ ፡ ከርሱ ፡ አይቀበል ፡ ይበል ።
ከወንድሙ ፡ ጋር ፡ ቂም ፡ በቀል ፡ ያለበት ፡ የዝ
ሙት ፡ የስካር ፡ አሳብ ፡ በውስጡ ፡ ያለበት ፡

አንቀጽ ፡ ፲፫ ።

በረ ፡ በጥንተ ፡ ቅዳሴ ፡ ኢይቅረብ'' ።

፬፻፺፮ ክርስጢ ፡ ወኢይደልዎ ፡ ለቀሲስ ፡ ዘኢነበረ ፡ በጥንተ ፡ ቅዳሴ ፡ ከመ ፡ ይትመጠው ፡ ቍርባነ ፡ አው ፡ ይንሣእ ፡ በእዴሁ ፡ እምሥጋ ፡ ቅዱስ ፡ ወደሙ ፡ ንቡር ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅብጣዊት ፡ ፫ቱ ፡ ቅዳሴያት ፡ ዘባስልዮስ ፡ ወጎርጎርዮስ ፡ ወቄርሎስ ፡ ወተገብሮት ፡ ኪያሆሙ ።

ስለ ፡ ቍርባን ።

ቅዳሴው ፡ ሲጀመር ፡ ያልነበረ ፡ አይቁረብ ፡ ይበል ።

፬፻፺፮ ክርስጢ ፡ ቅዳሴው ፡ ሳይጀመር ፡ ያልነበረ ፡ ቄስ ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ወይም ፡ ቅዱስ ፡ ሥጋውን ፡ በእጁ ፡ አንሥቶ ፡ መቀበል ፡ አይገባውም ፡ አነሆ ፡ በግብጽ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የባስልዮስ ፡ የጎርጎርዮስ ፡ የቄርሎስ ፡ ፫ት ፡ ቅዳሴዎች ፡ ተጽፈዋል ፡ እነሱን ፡ መቀደስ ፡ ነው ።

## አንቀጽ ፡ ፲ወ፫ቱ ።

በእንተ ፡ ቍርባን ።

፬፻፺፯ ረስጠብ ፡ ፪ቱ ፡ ኢያብእ ፡ ካህን ፡ ውስተ ፡ ምሥዋዕ ፡ ቅዱስ ፡ መዓረ ፡ ወኢሐሊበ ፡ ወኢያሬ ፡ ወኢሥጋ ፡ እንስሳ ፡ ካልእ ። እመቦ ፡ ካህን ፡ ዘቦአ ፡ በምንትኒ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘአዘዞ ፡ እግዚእ ፡ ይትመተር ፡ ዘእንበለ ፡ ዘይት ፡ ንጹሕ ፡ ስአብርሆ ፡ ወዕጣን ፡ በጊዜ ፡ ቅዳሴ ፡ ንጹሕ ።

፬፻፺፰ ጴጥ ፡ ረስጠጅ ፡ ፫ቱ ፡ ወኢያዕርጉ ፡ ላዕለ ፡ ምሥዋዕ ፡ ዘእንበለ ፡ ኅብስተ ፡ ሥርናይ ፡ ንጹሕ ፡ ወማየ ፡ ወይን ፡ ንጹሕ ፡ ወኢይወልጡ ፡ ወይነ ፡ በምንትኒ ፡ እምአምያስ ፡ ዘያስክሩ ፡ ወዘይትገበሩ ፡ በእሳት ። ወያብእ ፡ ካዕበ ፡ ፍሬ ፡ ስዊት ፡ በጊዜሁ ፡ ወአስካለ ፡ ወይን ፡ እመ ፡ በዓሉ ፡ ዘቀዳሚ ፡ በጽሐቱ ።

፬፻፺፱ በስ ፡ ፺ወ፱ቱ ፡ ወይኩን ፡ ቍርባን ፡ እምንዋየ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ። ወለአመሰ ፡ አልቦቱ ፡ ንዋይ ፡ ዘይገብር ፡ ወያስተዳልዉ ፡ እምዘአብእ ፡ ውስቴታ ።

፭፻ ድስቅ ፡ ፴ወ፰ቱ ፡ ወያዕርጉ ፡ ቍርባነ ፡ በኵሉ ፡ ሰሙን ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ ወረቡዕ ፡ ወዓርብ ፡ ወሰንበት ፡ ወበዕለተ ፡ በዓላት ፡ አመ ፡ የኀብር ፡ በውስቴ ፡ ማእከሉ ።

፭፻፩ ዘኟወ፩ዱ ፡ ወኢያዕርጉ ፡ ቍርባነ ፡ እንበለ ፡ ቍርባነ ፡ ምእመናን ፡ ወኢይትወከፉ ፡ መባአሙ ፡ ለጸራፍያን ፡ ወለቀታልያን ፡ ወዘማውያን ፡ ወመመጠዓውያን ፡ ወሰራቅያን ፡ ወገባርያን ፡ ጣዖታት ፡ ወሰካርያን ፡፡ ወለእለ ፡ ያጽዕቁ ፡ ላዕለ ፡ ስቡራት ፡ ወእጓለ ፡ ማውታ ፡ ወመጻብሐን ፡ ወሀያድያን ፡ ወዓማፅያን ። ወእምነ ፡ ሐራ ፡ እለ ፡ የሀውኩ ፡ ነዳያነ ፡ ወእለ ፡ ይሞቅሕዎሙ ፡ ለሰብእ ፡ በዓመፃ ፡ ወእለ ፡ ይቀንዩ ፡ አግብርቲሆሙ ፡ ቅንየተ ፡ እኩየ ፡ ወእለ ፡ የሐሥሙ ፡ ላዕ

## አንቀጽ ፡ ፲፫ ።

ስለ ፡ ቍርባን ።

፬፻፺፯ ረስጠብ ፡ ፪ ፡ ካህኑ ፡ ወደቤተ ፡ መቅደስ ፡ መዓር ፡ ወተት ፡ ዎፍ ፡ ሌላም ፡ የእንስሳ ፡ ሥጋ ፡ አያግባ ። ጌታ ፡ ካዘዘው ፡ በቀር ፡ ማናቸውንም ፡ ይዞ ፡ የገባ ፡ ካህን ፡ ቢኖር ፡ ይሻር ። ለማብራት ፡ ከንጹሕ ፡ ዘይትና ፡ በቅዳሴ ፡ ጊዜም ፡ ከንጹሕ ፡ ዕጣን ፡ በቀር ።

፬፻፺፰ ጴጥ ፡ ረስጠጅ ፡ ፫ ፡ ንጹሕ ፡ ከሆነ ፡ ከስንዴ ፡ ንጹሕ ፡ ከሆነም ፡ ከወይን ፡ በቀር ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አይሠዉ ፡ በእሳት ፡ ከሚበስሉ ፡ ከሚያሰክሩ ፡ መጠጦች ፡ ወገን ፡ በማናቸውም ፡ ወይኑን ፡ እይለውጡ ። ዳግመኛም ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የደረሰውን ፡ የወይን ፡ ዘለላ ፡ የእሸቱን ፡ ፍሬ ፡ ያግቡ ።

፬፻፺፱ በስ ፡ ፺፱ ፡ ቍርባኑ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ገንዘብ ፡ ይሁን ፡ ገንዘብ ፡ ባይኖራት ፡ ግን ፡ ከአስገቡት ፡ ወገን ፡ አዘጋጅተው ፡ ይሠዉ ።

፭፻ ድስቅ ፡ ፴፰ ፡ በሳምንቱ ፡ ሁሉ ፡ እሑድ ፡ ረቡዕና ፡ ዓርብ ፡ ቅዳሜ ፡ በመካከል ፡ በዓል ፡ በዋለ ፡ ጊዜ ፡ በበዓላት ፡ ቀን ፡ መሥዋዕት ፡ ይሠዉ ።

፭፻፩ ኛ፩ ፡ ከደጋጎቹ ፡ ምእመናን ፡ ቍርባን ፡ በቀር ፡ መሥዋዕት ፡ አይሠዉ ፡ የተሳዳቢዎችን ፡ የነፍስ ፡ ገዳዮችን ፡ የሴሰኞችን ፡ የጣዖት ፡ እምላኪዎችን ፡ የሌቦችን ፡ ጣዖት ፡ የሚሠሩትን ፡ የሰካራሞችን ፡ ባልቴቶችንና ፡ ድሀ ፡ አደጎችን ፡ የሚያስቸግሩትን ፡ የቀራጮችን ፡ የቀማኞችን ፡ የዓመፀኞችን ፡ መባዕ ፡ አይቀበሉ ። ድሆችን ፡ የሚያስቸግሩ ፡ ጭፍሮች ፡ በግድ ፡ ሰዎችን ፡ ከሚያስሯቸው ፡ ባሮቻቸውን ፡ በክፉ ፡ አገዛዝ ፡ ከሚገዟቸው ፡ ክፋትም ፡ ከሚያደርጉባ

ሌሆሙ ፡ ወእለ ፡ ይዔምፁ ፡ በግፍዕ ። ወነጋድ
ያን ፡ እለ ፡ ይሠይጡ ፡ ቶሲሐሙ ፡ ማየ ፡ በወ
ይን ። ወኵሎሙ ፡ ዐላውያን ፡ ሕግ ፡ እስመ ፡
እግዚአብሔር ፡ ይሜንን ፡ መሥዋዕተ ፡ ረሲ
ዓን ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ሰሎሞን ፡ ጠቢብ ።

፳፻፪ ዘኒቅያ ፡ ፴ ፡ ኢትሚጥ ፡ ብኵርናከ ፡ አ ፡ ካህን ፡
በተመጥዎተ ፡ ምንትኒ ፡ እምዘውእቱ ፡ ዘልሙ ፡
ላዕለ ፡ ዕልወቱ ።

፳፻፫ ዘኒቅያ ፡ ፴ ፡ ወኢትትወከፍ ፡ ካዕበ ፡ ቍርባ
ናተ ፡ ስዱዳን ፡ እለ ፡ አሰረቶሙ ፡ ቤተ ፡ ክርስ
ቲያን ።

፳፻፬ ድስቅ ፡ ፴ወ፫ቱ ፡ ረስጠብ ፡ ፵ወ፬ቱ ፡ ወኢይቅ
ረብ ፡ እንበለ ፡ ምእመናን ፡ ወዘኢተሰደ ።

፳፻፭ ዘስንቆራ ፡ ፲ወ፩ ፡ እመበ ፡ እምእመናን ፡ ዘኮነ ፡
ውጉዘ ፡ ምስለ ፡ እፍአውያን ፡ ለእመ ፡ ቀርበት ፡
ዕለተ ፡ ሞቱ ፡ ኢይክልእዎ ፡ ቍርባነ ። ወለእመ
ጥዕየ ፡ እምደዌሁ ፡ ይሳተፍ ፡ ምስለ ፡ ምእመ
ናን ፡ በጸሎት ፡ ወኢይትመየጥ ፡ ኀበ ፡ መዓርገ ፡
እፍአውያን ።

፳፻፮ ጢሞ ፡ ወለዘአኀዞ ፡ ጋኔን ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘኢያ
ዐርፍ ፡ ወዘኢያሴውና ፡ ምሬቶ ፡ እምድኅረ ፡
ተነጽሖቱ ፡ የሀብዎ ፡ ቍርባነ ፡ በበዓላት ።

፳፻፯ ድስቅ ፡ ፴ወ፩ቱ ፡ ወይጽሐፉ ፡ ዲያቆናት ፡
ኵሎ ፡ ዕለተ ፡ አስማቲሆሙ ፡ ለእለ ፡ አምጽኡ ፡
ቍርባነ ፡ እመ ፡ ኮኑ ፡ ሕያዋነ ፡ አው ፡ ምዉ
ታነ ፡ ከመ ፡ ይዝክርዎሙ ፡ በጊዜ ፡ ጸሎት ፡ ወእ
ንብበ ፡ ወይኩኑ ፡ መዘምራን ፡ ውስተ ፡ ውሳጤ፡
መንጦላዕት ፡ ወኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ ኅቡረ ፡ ይስ
አሉ ፡ ሎሙ ።

፳፻፰ ረስጣ ፡ ፴ ፡ ወይኩን ፡ ኅብስተ ፡ ቍርባን ፡ ዘያዐ
ርጉ ፡ ላዕለ ፡ ምሥዋዕ ፡ ኅብስተ ፡ ዕለት ፡ ወኢይ
ቢት ፡ ለጊሠም ፡ ወይክፍልዎ ፡ በዕለቱ ፡ ወኢ
ያትርፉ ፡ እምኔሁ ፡ ምንተኒ ፡ ለዕለት ፡ ካል
እት ። በስ ፡ ፺ወ፫ቱ ፡ ወኢይኩን ፡ ዘቦቱ ፡ ንቅ
ዓት ፡ እላ ፡ ድኁነ ፡ እምነውር ።

፳፻፱ ዘ፺ወ፱ቱ ፡ ወይደይዎ ፡ ለወይን ፡ ውስተ ፡
ጽዋዕ ፡ ወያስተሐይጹ ፡ ወኢያስርጉ ፡ እምኔሁ ፡
ዘእንበለ ፡ ስእመ ፡ ኢኮነ ፡ ጽሩየ ፡ ወንጹሐ ።

፳፻፲ ፻ወ፪ቱ ፡ ወዘይሠርዕ ፡ ጽዋዐ ፡ ኢይደይ ፡ ወይነ ፡
ብሉየ ፡ ወኢይቶስሕ ፡ ማየ ፡ ብዙኀ ፡ ዘይፈደ



ቸው ፡ በግፍ ከሚበድሉ ፡ ሰዎች ፡ ወገን ፡ መባዕ
(መሥዋዕት) ፡ አይቀበሉ ። ከወይኑ ፡ ውሀ ፡
ጨምረው ፡ ከሚሸጡ ፡ ነጋዴዎች ፡ ሕግን ፡
ከሚያፈርሱ ፡ ሁሉ ፡ አይቀበሉ ። ብልሁ ፡ ሰሎ
ሞን ፡ እንደተናገረ ፡ እግዚአብሔር ፡ የኃጢአተ
ኞችን ፡ መሥዋዕት ፡ ይጸየፋልና ። (ምሳ ፡ ፲፭ ፡
፰) ።

፳፻፪ ኒቅያ ፡ ፴ ፡ ካህን ፡ ሆይ ፡ በክህደት ፡ካለ ፡ ሰው ፡
ምንምን ፡ በመቀበል ፡ መዓርግህን ፡ አትሽጥ ።

፳፻፫ ኒቅያ ፡ ፴ ፡ ዳግመኛም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
አውግዛ ፡ የለየቻቸውን ፡ ሰዎች ፡ መሥዋዕት ፡
አትቀበል ።

፳፻፬ ድስቅ ፡ ፴፫ ፡ ረስጠብ ፡ ፵፬ ፡ ከምእመናንና ፡
ካልተወገዘ ፡ ሰው ፡ በቀር ፡ አይቍረብ ።

፳፻፭ ስንቄራ ፡ ፲፩ ፡ ከምእመናን ፡ ወገን ፡ ከተወገዙ ፡
ሰዎች ፡ ጋር ፡ የተወገዘ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ የሚሞ
ትበት ፡ ቀን ፡ ቢደርስ ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡
አይከልክሉት ። ከደዌው ፡ ቢድን ፡ ከምእመናን
ጋር ፡ በጸሎት ፡ ይገናኝ ። ወደ ፡ ተወገዙት ፡
ሰዎች ፡ ቦታ ፡ አይመለስ ።

፳፻፮ ጢሞ ፡ ጋኔን ፡ የያዘው ፡ ሰው ፡ የማይሳይብ ፡
ከሚስለውም ፡ በኋላ ፡ ምሬቱን ፡ የማያሰላግገው ፡
ከሆነ ፡ በበዓላት ፡ ቀን ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡
ያቀብሉት ።

፳፻፯ ድስቅ ፡ ፴፩ ፡ ዲያቆናት ፡ መባስ ፡ የሚያመጡ
ትን ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ ሁልጊዜ ፡ ይጻፉ ፡ ሕያዋን ፡
ወይም ፡ ሙታንም ፡ ቢሆኑ ፡ በጸሎትና ፡ በድ
ጋም ፡ ጊዜ ፡ ይጠሯቸው ፡ ዘንድ ፡ መዘምራ
ኑም ፡ በመጋረጃው ፡ ውስጥ ፡ ይሁኑ ፡ ሕዝቡ ፡
ሁሉ ፡ ይለምኑላቸው ።

፳፻፰ ረስጣ ፡ ፴ ፡ በታቦቱ ፡ ላይ ፡ የሚሠዉትን ፡
መሥዋዕት ፡ ስለቱን ፡ ያዘጋጁት ፡ ይሁን ፡ ለነ
ገው ፡ አያድር ፡ ዕለቱን ፡ ይክፈሉት ፡ ለሌላው ፡
ቀን ፡ ከርሱ ፡ ምንም ፡ አያትርፉ ፡ (አያሳድሩ) ።
በስ ፡ ፺፫ ፡ መሥዋዕቱ ፡ ንቃት ፡ ያለበት ፡ አይ
ሁን፡ ነውር ፡ የሌለበት ፡ ይሁን ፡ እንጂ ።

፳፻፱ ፺፱ ፡ ወይኑን ፡ ወደ ፡ ጽዋው ፡ ውስጥ ፡ ይገልብ
ጡት ፡ ይመልከቱትም ፡ እርሱ ፡ ንጹሕ ፡ ጥሩ ፡
ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አያሥዉ ።

፳፻፲ ፻፪ ፡ ጽዋውን ፡ የሚያዘጋጀው ፡ ሰው ፡ ጊዜ ፡
ያለፈውን ፡ ወይን ፡ አይጨምር ፡ ከሦስት ፡ እጅ

ፍድ ፡ እምኀልስተ ፡ እድ ፡ ወለእመ ፡ ተረክበ ፡ ወይን ፡ ብዙኀ ፡ ይቶስሕ ፡ ዓሥራተ ፡ እደ ፡ እማይ ፡ ወኢያፍልስ ፡ እምዓቅመ ፡ ዝንቱ ፡ መድሎት ። ወለእመ ፡ ተሀበለ ፡ ወእፍለሰ ፡ ይፃእ ።

፩፻፲፩ ረስጣ ፡ ፵ወ፳ቱ ፡ ወኢይምላእ ፡ ጽዋዐ ፡ እስከ ፡ ከንፈሩ ፡ ምልአተ ፡ ዘይፈደፍድ ፡ ከመ ፡ ኢይትከዐው ፡ እምኔሃ ፡ ምንትኒ ፡ ዲበ ፡ ምድር ።

፩፻፲፪ ረስጠብ ፡ ፵ወ፮ቱ ፡ ጴጥ ፡ ወኢይንሣእ ፡ መኑሂ ፡ ቍርባነ ፡ ዘእንበለ ፡ ይጹም ፡ በንጹሕ ፡ ወእመበ ፡ ዘጥዕመ ፡ እምእመናን ፡ ወእምእመናት ፡ ወእምዝ ፡ ተመጠወ ፡ ወለእመ ፡ ገብረ ፡ ዘንተ ፡ በተሃብሎ ፡ ይሰደድ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እስከ ፡ ለዓለም ።

፩፻፲፫ በደስ ፡ ፳ወ፫ቱ ፡ ረስጠብ ፡ ፵ወ፫ቱ ፡ ወኵሉ ፡ ምእመን ፡ ያመክር ፡ ርእሶ ፡ ከመ ፡ ይትመጠው ፡ እምሥጢራት ፡ እምቅድመ ፡ ይጥዓም ፡ ምንተኒ ፡ ፈድፋደሰ ፡ በመዋዕለ ፡ ጾም ። ወለእመ ፡ ቦቱ ፡ ሃይማኖት ፡ ይትመጠዎ ፡ ወሶበ ፡ ወሀቦ ፡ መኑሂ ፡ ሕምዘ ፡ ዘይቀትል ፡ እልቦ ፡ ዘየሐምም ፡

፩፻፲፬ ዘ፵ወ፬ቱ ፡ ወያስተሐምም ፡ ኵሉ ፡ ለለ፩ዱ ፡ በጽኑዕ ፡ ከመ ፡ ኢይትመጠ ፡ መኑሂ ፡ ዘእንበለ ፡ ምእመናን ፡ እምሥጢራት ። ዝየ ፡ ነበረ ፡ ውስተ ፡ ፩ዱ ፡ እምቀኖናት ፡ ዘለነገሥት ፡ ይደልዎሙ ፡ ለምእመናን ፡ እደው ፡ ወአንስት ፡ ከመ ፡ ይቁሙ ፡ ውስተ ፡ ጸሎተ ፡ ቍርባናት ፡ በእገሪሆሙ ፡ ለሀለም ፡ እንዘ ፡ ይሴብሑ ፡ ወእንዘ ፡ የኀሥሡ ፡ ወይትዐቀቡ ፡ እምነገር ፡ በውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

፩፻፲፭ ጅ ፡ ፯ቱ ፡ ወለእመ ፡ አቅረበ ፡ መባአ ፡ ውስተ ፡ ምሥዋዕ ፡ ወተዘከረ ፡ ከመ ፡ እኁሁ ፡ ዘየኀዝን ፡ ላዕሌሁ ፡ ይኅድግ ፡ መባአ ፡ ቅድመ ፡ ምሥዋዕ ፡ ወይሑር ፡ ቅድመ ፡ ወይትዐረቅ ፡ ምስለ ፡ እኁሁ ፡ ውእተ ፡ ጊዜ ፡ ይምጻእ ፡ ወያቅርብ ፡ መባአ ።

፩፻፲፮ ዘቆሮንቶስ ፡ ፲ወ፬ቱ ፡ ወዘይበልዕ ፡ እምሥጋ ፡ እግዚእ ፡ ወዘይሰቲ ፡ እምደሙ ፡ እንዘ ፡ ኢይደልዎ ፡ መአብስ ፡ ውእቱ ፡ ላዕለ ፡ ሥጋ ፡ እግዚእነ ፡ ወደሙ ፡ ክቡር ። በእንተዝ ፡ ያመክር ፡ ብእሲ ፡ ነፍሶ ፡ ቅድመ ፡ ወያሠንያ ፡ ወእምዝ ፡ ይብላዕ ፡ እምዝንቱ ፡ ኅብስት ፡ ወይስተይ ፡ እምዝንቱ ፡ ጽዋዕ ። እስመ ፡ ዘይበልዕ ፡ ወይሰቲ ፡ እምኔሁ ፡ እንዘ ፡ ኢይደልዎ ፡ በልዐ ፡ ወሰ



የበለጠ ፡ ብዙ ፡ ውኃ ፡ አይጨምር ፡ ብዙ ፡ ወይን ፡ (ዘቢብ) ቢገኝ ፡ ከውኃው ፡ አሥር ፡ እጅ ፡ ይጨምር ፡ ከዚህ ፡ ከተወሰነው ፡ ልክ ፡ አያብልጥ ፡ አያሳንስ ፡ ይህን ፡ ተደፋፍሮ ፡ ቢያበልጥ ፡ ቢያሳንስ ፡ ይለይ ።

፩፻፲፩ ረስጣ ፡ ፵፳ ፡ ጽዋውን ፡ እስከ ፡ ከንፈሩ ፡ ድረስ ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ አይሙላው ፡ ደሙ ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ እንዳይፈስ ።

፩፻፲፪ ረስጠብ ፡ ፵፮ ፡ ጴጥ ፡ በሚገባ ፡ ሳይጾም ፡ ማንም ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ አይቀበል ፡ ከወንዶችም ፡ ከሴቶችም ፡ ወገን ፡ የቀመሰ ፡ ቢኖር ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ቢቀበል ፡ ይህንንም ፡ በድፍረት ፡ ቢያደርግ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እስከ ፡ ዘለዓለሙ ፡ ድረስ ፡ ይለይ ።

፩፻፲፫ በደስ ፡ ፳፫ ፡ ረስጠብ ፡ ፵፫ ፡ ምእመን ፡ ሁሉ ፡ ምንም ፡ ከመቅመሱ ፡ አስቀድሞ ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ ራሱን ፡ ይመርምር ፡ ይልቁንም ፡ በጾም ፡ ወራት ፡ ሃይማኖት ፡ ያለው ማንም ፡ ማን ፡ የሚገድል ፡ መርዝ ፡ በሰጠው ፡ ጊዜ ፡ ቢቀበለው ፡ የሚጎዳው ፡ ነገር ፡ የለም ።

፩፻፲፬ ፵፬ ፡ ከምእመናን ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ እንዳይቀበል ፡ ሁሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ ፈጽሞ ፡ ይትጋ ። ለነገሥታት ፡ ከተጻፉት ፡ ሕጎች ፡ ወገን ፡ በአንዱ ፡ ከዚህ ፡ ተጻፈ ። ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ምእመናንም ፡ በጸሎት ፡ ጊዜና ፡ በቍርባን ፡ ጊዜ ፡ በእግራቸው ፡ መቆም ፡ ይገባቸዋል ። እያመሰገኑ ፡ ሥርዓትን ፡ እየፈለጉ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ከነገር ፡ ይጠበቁ ።

፩፻፲፭ ጅ ፡ ፯ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መባዕ ፡ ቢያቀርብ ፡ ወንድሙ ፡ እንዳዘነበት ፡ ቢያስብ ፡ መባውን ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደጃፍ ፡ ትቶ ፡ አስቀድሞ ፡ ሂዶ ፡ ከወንድሙ ፡ ጋር ፡ ይታረቅ ፡ ያን ፡ ጊዜም ፡ መጥቶ ፡ መባውን ፡ ያቅርብ ፡ (ማቴ ፡ ፭ ፡ ፳፫ - ፳፬) ።

፩፻፲፮ ቆሮንቶስ ፡ ፲፬ ፡ ሳይገባው ፡ የጌታን ፡ ሥጋ ፡ የበላ ፡ ደሙንም ፡ የጠጣ ፡ በጌታችን ፡ ሥጋና ፡ በክቡር ፡ ደሙ ፡ ላይ ፡ በደለኛ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ሰው ፡ አስቀድሞ ፡ ሰውነቱን ፡ መርምሮ ፡ ንጹሕ ፡ ያድርግ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከዚህ ፡ እንጀራ ፡ ይብላ ፡ ከዚህም ፡ ወይን ፡ ይጠጣ ፡ ሳይገባው ፡ ከርሱ ፡ የበላ ፡ የጠጣ ፡ የሰውነቱን ፡ ጥፋት ፡ በላ ፡ ጠጣ ፡ እኮ ፡ የጌታችንን ፡ ሥጋ ፡

ትየ ፡ ኅሎለ ፡ ለንፍስ ፡ እስመ ፡ ኢያእመረ ፡
ሥጋ ፡ እግዚእነ ፡ ወኢፈለጠ ፡ እምኅልአ ። በእ
ንተ ፡ ዝንቱ ፡ በዝኑ ፡ እምውስቴትክሙ ፡ ሕሙ
ማን ፡ ወድዉያን ፡ ወእለ ፡ ይመውቱ ፡ ግብተ ።

፳፻፲፯ ሥርዐት ፡ እምአሪት ፡ እመቦ ፡ ዘበልዐ ፡ እመሥ
ዋዕተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወውእቱ ፡ እንዘ ፡
ርኩስ ፡ ትሥሮ ፡ ይእቲ ፡ ነፍስ ፡ እምሕዝባ ።

፳፻፲፰ ረስጠብ ፡ ፯ቱ ፡ ረስጠጅ ፡ ፰ቱ ፡ ወሶበ ፡ አዕረገ ፡
ቍርባነ ፡ ወኢተመጠወ ፡ እምኔሁ ፡ ኤጲስቆ
ጶስ ፡ አው ፡ ፩ዱ ፡ እምካህናት ፡ ይንግር ፡ ምክን
ያተ ፡ ዘበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ወሶበ ፡ ነገረ ፡ ይሥ
ረዩ ፡ ሎቱ ። ወለእመ ፡ ኢነገረ ፡ ይትፈለጥ ፡
እስመ ፡ ውእቱ ፡ ኮነ ፡ ምክንያተ ፡ ለኑፋቄ ፡
ሕዝብ ፡ በዐዊረ ፡ ቍርባን ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡
ኢያርር ፡ በንጽሕ ።

፳፻፲፱ ረስጣ ፡ ፶ወ፫ቱ ፡ ዘኒቅያ ፡ ፲ወ፯ቱ ፡ ወይትመጠው ፡
ቅድመ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ቍርባነ ። ወእምድኅ
ሬሁ ፡ ይትመጠዉ ፡ ቀሳውስት ፡ ወዲያቆናት ፡
ወእምድኅሬሆሙ ፡ ኵሎሙ ፡ ሕዝብ ፡ ወእምድ
ኅረ ፡ እደው ፡ ይትመጠዋ ፡ አንስት ፡ ወይዕዘ
ምሩ ፡ በጊዜ ፡ ተመጥዎ ፡ ቍርባን ፡ ኵሎሙ ፡
ምእመናን ።

፳፻፳ ረስጣ ፡ ፶ወ፫ቱ ፡ በስ ፡ ፺ወ፱ቱ ፡ ወይበል ፡
ካህን ፡ ጊዜ ፡ ይሜጡ ፡ ሥጋ ፡ "ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡
ሥጋሁ ፡ ለክርስቶስ ፡ ዘመጠዎ ፡ በእንተ ፡ ኃጢ
ውኢነ ። ወይበል ፡ ዘይትሜጠው ፡ አሜን ። ወከ
ማሁ ፡ ይበል ፡ ካዕበ ፡ ዘያእኅዝ ፡ ጽዋዐ ፡ ዝ ፡
ውእቱ ፡ ደሙ ፡ ለክርስቶስ ፡ ዘተክዕወ ፡ በእን
ቲአነ" ። ወይበል ፡ ዘይትሜጠው ፡ አሜን ፡ ወአ
ሜን ፡ ወይትመጠዎ ፡ በፍርሃት ፡ ዐቢይ ፡ ወን
ጽሕ ።

፳፻፳፩ ረስጣ ፡ ፶ወ፫ቱ ፡ ወይትዓቀቡ ፡ ቀሳውስት ፡
ወዲያቆናት ፡ ከመ ፡ ኢይትርፍ ፡ ምንትኒ ፡ እም
ቍርባን ፡ ወይከዉን ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ኵነኔ ፡
ዐቢይ ።

፳፻፳፪ በስ ፡ ፺ወ፱ቱ ፡ ወለዘተርፈ ፡ እምጽዋዕ ፡ ይት
መጠውዎ ፡ ኵሎሙ ፡ ዲያቆናት ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡
ውስተ ፡ ምሥዋዕ ።

፳፻፳፫ ዘያት ፡ ወይትዐቀብ ፡ ኵሉ ፡ ለለ፩ዱ ፡ ከመ ፡
ኢይትርፍ ፡ ምንትኒ ፡ ፈቀዶ ፡ ከመ ፡ ይብልዖ ፡
ከመ ፡ መብልዕ ፡ ሥጋዊ ፡ ከመ ፡ ኢይኩን ፡ ላዕ
ሌሆሙ ፡ ዘኮነ ፡ በደቂቀ ፡ አሮን ፡ ወደቂቀ ፡
ዔሊ ፡ ሶበ ፡ አስተቃለሉ ፡ መሥዋዕተ ፡ እግዚአ

እውቆ ፡ ከሌላው ፡ አለየውምና ። ከእናንተ ፡
ወገን ፡ ሕመምተኞችና ፡ ድውያኖች ፡ በድንገ
ትም ፡ የሚሞቱ ፡ በዝተዋል ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡
፳፱ - ፴) ።

፳፻፲፯ ከኦሪት ፡ የተገኘ ፡ ሥርዓት ፡ ኃጢአተኛ ፡ ሳለ ፡
የእግዚአብሔርን ፡ መሥዋዕት ፡ የበላ ፡ ቢኖር ፡
ይህች ፡ ነፍስ ፡ ከወገኗ ፡ ትለይ ።

፳፻፲፰ ረስጠብ ፡ ፯ ፡ ረስጠጅ ፡ ፰ ፡ መሥዋዕት ፡ በሠዋ
ጊዜ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሱ ፡ ወይም ፡ ከካህናት ፡
ወገን ፡ አንዱ ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ባይቀ
በል ፡ የማይቀበልበትን ፡ ምክንያት ፡ ይናገር ፡
ቢናገር ፡ ይቅር ፡ ይበሉት ። ባይናገር ፡ ይለይ ።
ባቀረበው ፡ ቍርባን ፡ እርሱ ፡ በንጽሕና ፡ እንዳ
ላቀረበው ፡ ሕዝቡን ፡ ለማጠራጠር ፡ እርሱ ፡
ምክንያት ፡ ሁኗልና ።

፳፻፲፱ ረስጣ ፡ ፶፫ ፡ ኒቅያ ፡ ፲፯ ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ አስቀ
ድሞ ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ይቀበል ፡ ከዚ
ህም ፡ ቀጥሎ ፡ ቀሳውስትና ፡ ዲያቆናት ፡
ይቀበሉ ፡ ከእነርሱ ፡ ቀጥለው ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡
ይቀበሉ ፡ ከወንዶችም ፡ ቀጥለው ፡ ሴቶች ፡
ይቀበሉ ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ በተቀበሉ ፡
ጊዜ ፡ ምእመናን ፡ ሁሉ ፡ ይመስግኑ ።

፳፻፳ ረስጣ ፡ ፶፫ ፡ በስ ፡ ፺፱ ፡ ካህኑ ፡ ሥጋውን ፡ በሚ
ያቀብልበት ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ኃጢአታችን ፡ የተሰጠ
የክርስቶስ ፡ ሥጋ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ይበል ።
የሚቀበለውም ፡ አሜን ፡ ይበል ፡ ዳግመኛም ፡
ጽዋውን ፡ ይዞ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ የፈሰሰ ፡ የክርስ
ቶስ ፡ ደም ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ይበል ። የሚቀበለውም
አሜን ፡ አሜን ፡ ይበል ። በፍጹም ፡ ፍርሃትና ፡
በንጽሕና ፡ ይቀበለው ።

፳፻፳፩ ረስጣ ፡ ፶፫ ፡ ቀሳውስትና ፡ ዲያቆናት ፡ ከሥጋ
ውና ፡ ከደሙ ፡ ምንም ፡ እንዳይቀር ፡ ይጠን
ቀቁ ፡ ፍጹም ፡ ቅጣት ፡ ይዘንባቸዋል ።

፳፻፳፪ በስ ፡ ፺፱ ፡ ከደሙም ፡ የቀረውን ፡ በቤተ ፡ ክር
ስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ዲያቆናት ፡ ሁሉ ፡
ይቀበሉት ።

፳፻፳፫ ፫ ፡ ሁሉ ፡ ለእያንዳንዱ ፡ እንደ ፡ ሥጋዊ ፡
መብል ፡ ሊበላው ፡ በወደደ ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ እን
ዳያስቀር ፡ ይጠንቀቅ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መሥ
ዋዕት ፡ ባቃለሉ ፡ ጊዜ ፡ በአሮን ፡ ልጆችና ፡
በዔሊ ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ እንዳይደ

ብሔር ።

፩፻፹፬ ረስጣ ፡ ፶ወ፫ቱ ፡ ወሶበ ፡ ፈጸሙ ፡ መዘምራን ፡ ስባሒሆሙ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ ይበል ፡ ዲያቆን ፡ በልዑል ፡ ቃል ፡ "ተመጠነ ፡ እምሥጋ ፡ ክርስቶስ ፡ ክቡር ፡ ወናእኰቶ ፡ ለዘረሰየነ ፡ ድልዋነ ፡ ለተመጥዎቱ" ። ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ይጸሊ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እንዘ ፡ የአኵቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ነሢአተ ፡ ምሥጢር ፡ ቅዱስ ።

፩፻፹፭ ወሶበ ፡ ፈጸመ ፡ ቀሲስ ፡ ጸሎቶ ፡ ይበል ፡ ዲያቆን ፡ "አድንኑ ፡ አርእስቲክሙ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ይባርክሙ" ። ወይበል ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ጸሎተ ፡ ቡራኬ ፡ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ይበል ፡ ዲያቆን ፡ ሑሩ ፡ በሰላም ።

፩፻፹፮ በስ ፡ ፺ወ፯ቱ ፡ ወኢይትርፍ ፡ እምጽዋዕ ፡ ዘሥሩዕ ፡ እምድኅረ ፡ ፍጻሜ ፡ እኩቴት ፡ በእንተ ፡ ጸኒሖቱ ፡ ለዘኢመጽአ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በጊዜ ፡ ቅዳሴ ።

፩፻፹፯ ክርስጣ ፡ ፳ወ፩ቱ ፡ ኢያቀኵርር ፡ ፩ዱሂ ፡ ወኢይክድን ፡ ቍርባኖ ፡ በኀብስት ፡ እምቅድመ ፡ ስርሖት ፡ ወማየ ፡ መቍረርሂ ፡ ኢይንጦብ ፡ እምአፍ ፡ ምንትኒ ።

ንባቸው ። (፩ ፡ ሳሙ ፡ ፬ ፡ ፲፩ ። ዘሌ ፡ ፲ ፡ ፩-፫) ።

፩፻፹፬ ረስጣ ፡ ፶፫ ፡ መዘምራን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ምስጋና ፡ በጨረሱ ፡ ጊዜ ፡ ዲያቆኑ ፡ ቃሉን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ የክርስቶስ ፡ ክቡር ፡ ሥጋውን ፡ ተቀበልነ ፡ ይበል ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ለመቀበል ፡ ያበቃንን ፡ እናመስግነው ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ ቅዱስ ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ስለተቀበለ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያመሰገነ ፡ ይጸልይ ።

፩፻፹፭ ቄሱ ፡ ጸሎቱን ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ዲያቆኑ ፡ ያባርካችሁ ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ራሳችሁን ፡ ዝቅ ፡ አድርጉ ፡ ይበል ። ኤጲስቆጶሱ ፡ የቡራኬውን ፡ ጸሎት ፡ ይበል ፡ ከዚህም ፡ በኋላ፡ ዲያቆኑ ፡ በሰላም ፡ ሂዱ ፡ ይበል ፤

፩፻፹፮ በስ ፡ ፺፯ ፡ በቅዳሴ ፡ ጊዜ ፡ ወደቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያልመጣውን ፡ ሰው ፡ በመጠበቅ ፡ ከቅዳሴ ፡ በኋላ ፡ ከተሠዋዉ ፡ ደም ፡ አይትረፍ ።

፩፻፹፯ ክርስጣ ፡ ፳፩ ፡ አንዱስ ፡ እንኳ ፡ ከሰርሆተ ፡ ሕዝብ ፡ አስቀድሞ ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ በሌላ ፡ ኅብስት ፡ አያድፈው ፡ ማየ ፡ መቁረሩም ፡ ከአፉ፡ ምንም ፡ ጠብ ፡ አይበል ።

## አንቀጽ ፡ ፲ወ፩ቱ ።

በእንተ ፡ ጸሎት ።

፩፻፹፰ ጸሎትስ ፡ ይእቲ ፡ ተናግሮተ ፡ ሰብእ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ እንዘ ፡ የአኵቶ ፡ ወይሴብሖ ፡ ወይትአመን ፡ በእግዚእናሁ ፡ ወበተአምኖ በአበሳሁ ፡ ወኀሢሥ ፡ እምኔሁ ፡ በዘያሠምሮ ፡ ቦቱ ።

፩፻፹፱ ወለዘያጼሊ ፡ ሎቱ ፡ ሥርዓታት ፡ መቅድመ ፡ ኵሉ ፡ ከመ ፡ ይቁም ፡ በእገሪሁ ፡ ከመ ፡ ባህለ ፡ እግዚእነ ። ወሶበ ፡ ተንሣእክሙ ፡ ለጸልዮ ፡ ቁሙ ። ወቃለ ፡ ዳዊትኒ ፡ ዘይቤ ፡ "በጽባሕ ፡ እቀውም ፡ ቅድሜከ ፡ ወእስተርኢ ፡ ለከ" ።

፩፻፺ ወዳግሚት ፡ ቀኒተ ፡ ሐቌ ፡ በዝናር ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ ለይኩን ፡ ቅኑተ ፡ ሐቌክሙ ።

፩፻፺፩ ወሣልሲትኒ ፡ መይጠ ፡ ገጽ ፡ መንገለ ፡ ምሥራቅ ፡ እስመ፡ ውእቱ ፡ ገጽ ፡ ዘይቤ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ያስተርኢ ፡

## አንቀጽ ፡ ፲፩ ።

ስለጸሎት ።

፩፻፹፰ ጸሎትስ ፡ ሰው ፡ ከልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ጋር፡ የሚነጋገሩት ፡ ነገር ፡ ናት ። ፈጽሞ ፡ እያመሰገነ ፡ ጌትነቱን ፡ እምኖ ፡ በደሉን ፡ አምኖ ፡ እርሱን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝበትንም ፡ ሽቶ ።

፩፻፹፱ ለሚጸልይ ፡ ሰው ፡ ሥርዓቶች ፡ አሉት ፡ ጌታችን እንደተናገረ ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ በእግሮቹ ፡ ይቆም ፡ ዘንድ ፡ ለጸሎት ፡ በተነሣችሁ ፡ ጊዜ ፡ ቁሙ ፡ ዳዊትም ፡ "ማለዳ ፡ በፊትህ ፡ እቆማለሁ ፡ ለአንተም ፡ እታያለሁ ፡ አለ" (መዝ ፡ ፭ ፡ ፫) ።

፩፻፺ ሁለተኛዋ ፡ ጌታችን ፡ "ወገባችሁ ፡ የታጠቀ ፡ ይሁን ።" (ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፴፭) ። እንዳለ ፡ ወገብን ፡ በዝናር ፡ መታጠቅ ፡ ነው ።

፩፻፺፩ ሦስተኛዋም ፡ ፊትን ፡ ወደምሥራቅ ፡ መመለስ ፡ ነው ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባውና ፡ ክርስቶስ ፡ በዳግመኛ ፡ ምጽአቱ ፡ ጊዜ ፡ በርሱ ፡ ይገ

እንቀጽ ፡ ፲፬ ።

እመንገሌሁ ፡ እመ ፡ ምጽአቱ ፡ ዳግም ። ወበእንተ ፡ ዳዊት ፡ ነቢይ ፡ ዘ፳ወ፯ቱ ፡ ዘምሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘዐርገ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ። ወእምሰማይ ፡ ዘመንገለ ፡ ምሥራቅ ፡ አስምዐ ፡ ቃሎ ፡ ቃለ ፡ ኀይል ፡ ወእመንገለ ፡ ዛቲ ፡ ገጽ ፡ እንተ ፡ ተሰምዐ ፡ እምኔሃ ፡ ቃሉ ፡ ወእንተ ፡ እምኔሃ ፡ ይከውን ፡ ምጽአቱ ። ሠርዐት ፡ ሕግ ፡ ወአዘዘት ፡ ከመ ፡ ይሚጥ ፡ ኀቤሃ ፡ ገጾ ፡ ዘይጼሊ ። ወይደሉ ፡ ምስለ ፡ ዝንቱ ፡ ኀዲገ ፡ ተመይጦ ፡ ለፌ ፡ ወለፌ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አዘዞሙ ፡ ለደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ዘንተ ፡ በዕለተ ፡ ተናገሮሙ ።

፩፻፴፬ ወራብዕኒ ፡ አቲብ ፡ በአጽባዕት ፡ በአምሳለ ፡ መስቀል ፡ እመልዕልት ፡ ኀበ ፡ መትሕት ፡ ወእምፀጋም ፡ ኀበ ፡ የማን ። ወከዊነ ፡ አቲብስ ፡ በአጽባዕት ፡ በእንተ ፡ ሰዲደ ፡ አጋንንት ፡ ውእቱ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ ለእመ ፡ ኮንኩ ፡ አወፅእ ፡ አጋንንተ ፡ በአጽባዕተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወእመልዕልትስ ፡ እስከ ፡ መትሕት ፡ ወእምፀጋም ፡ እስከ ፡ የማን ፡ ዝኒ ፡ ትእምርተ ፡ ርደተ ፡ መድኀኒነ ፡ እምሰማይ ፡ ውስተ ፡ ምድር ። ወአፍልሶቱ ፡ ኪያነ ፡ እመንገለ ፡ ፀጋም ፡ ኀበ ፡ ገጸ ፡ የማን ። ወከዊነ ፡ አቲብኒ ፡ በአምሳለ ፡ መስቀል ፡ ዝኒ ፡ እስመ ፡ በመስቀሉ ፡ ፈጸመ ፡ አምላክ ፡ መድኀኒተ፡ ወዓዲ ፡ ከመ ፡ ንዘክር ፡ በዝንቱ ፡ ምሳሌ ፡ ጸጋሁ ፡ ለዘተሰቅለ ፡ በእንቲአነ ፡ ወሐዋርያትኒ ፡ ከማሁ ፡ አዘዙ ።

፩፻፴፭ ረስዓ ፡ ኃምሱ ፡ ከመ ፡ ንስትብ ፡ ፍጽማቲነ ፡ በአምሳለ ፡ መስቀል ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ በሃይማኖት ፡ ልባዊት ፡ ከመ ፡ ይርኀቅ ፡ ሰይጣን ፡ እምኔነ ። ወረሰዩ ፡ ዛተ ፡ ትእምርተ ፡ ላዕሌነ ፡ ከመ ፡ ንድኅን ፡ ባቲ ፡ እሙስና ፡ በከመ ፡ ረሰዮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለደመ ፡ በግዕ ፡ ዘፋሲካ ፡ ትእምርተ ፡ ውስተ ፡ አብያቲሆሙ ፡ ለደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ዘይከልእ ፡ ብድብደ ፡ ከመ ፡ ኢይቅትል ፡ እብኵሪሆሙ ፡ በከመ ፡ ቀተለ ፡ እብኵረ ፡ ግብጻውያን ። ወጊዜያተ ፡ ስትበትኒ ፡ በትእምርተ ፡ መስቀል ፡ ይእቲኬ ፡ ጥንተ ፡ ጸሎት ፡ ወጊዜ ፡ ይበጽሕ ፡ ተዘክሮተ ፡ መስቀል ።

፩፻፴፮ ወኃምስኒ ፡ አንብቦተ ፡ ቃላተ ፡ ጸሎት ፡ በፍርሃት ፡ ወበረዓድ ፡ ወአንብቦቱሂ ፡ ትኩን ፡ ዘባቲ ፡ ይከውን ፡ መንፈስ ፡ ዘያንሰሐስሕ ፡ መንገለ ፡ ፈጣሪ ። እመኒ ፡ በሕሊና ፡ ባሕቲቱ ፡ ወእመኒ ፡ በልሳን ፡ ከመ ፡ ይተርጕም ፡ ለሕሊና ።

ስለ ፡ ጸሎት ።

ለጽ ፡ ዘንድ ፡ የተነገረበት ፡ ነውና ። ነቢይ ፡ ዳዊትም ፡ ስለተናገረ ፡ ፳፯ ፡ ወደሰማይ ፡ ላረገው ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ ሰማይ ፡ የኀይል ፡ ቃሉን ፡ አሰማ ፡ በዚህችውም ፡ ቦታ ፡ ቃሉ ፡ የተሰማባት ፡ ምጽአቱም ፡ የሚደረግባት ፡ ናት ። የሚጸልይ ፡ ፊቱን ፡ ወደርሷ ፡ ይመልስ ፡ ዘንድ ፡ መጽሐፍ ፡ አዘዘች ። ከዚህም ፡ ጋር ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ መመላለስን ፡ መተው ፡ ይገባል፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ በተናገራቸው ፡ ቀን ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ አዟቸዋልና ።

፩፻፴፬ አራተኛውም ፡ በመስቀል ፡ አምሳል ፡ ከላይ ፡ ወደታች ፡ ከግራ ፡ ወደቀኝ ፡ በጣት ፡ ማማተብ ፡ ነው ። በጣት ፡ የማማተብ ፡ ሁኔታም ፡ አጋንንትን ፡ ለማባረር ፡ ነው ፡ ጌታችን ፡ "እኔ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ጣት ፡ አጋንንትን ፡ የማወጣ ፡ ከሆነ ፡ " (ሉቃ ፡ ፲፩ ፡ ፳) ብሎ ፡ እንደተናገረ ። ከላይ ፡ እስከታች ፡ ከግራ ፡ እስከ ፡ ቀኝ ፡ ማማተባችን ፡ ግን ፡ መድኃኒታችን ፡ ከሰማይ ፡ የመውረዱ ፡ እኛን ፡ ከግራ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ የመመለሱ ፡ ምልክት ፡ ነው ። በመስቀል ፡ አምሳል ፡ ማማተብም ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አምላክ ፡ በመስቀሉ ፡ ድኅነትን ፡ ፈጽሚልና ። ዳግመኛ ፡ በዚህ ፡ ምሳሌ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ የተሰቀለውን ፡ ቸርነት ፡ እናስብ ዘንድ ፡ ነው ፡ ሐዋርያትም ፡ እንደዚህ ፡ ብለው ፡ አዘዙ ።

፩፻፴፭ ረስጣ ፡ ኃምሱ ፡ ሰይጣን ፡ ከእኛ ፡ ይርቅ ፡ ዘንድ ፡ በተረዳች ፡ ሃይማኖት ፡ ዘወትር ፡ በመስቀል ፡ አምሳል ፡ ፊታችንን ፡ እናማትብ ፡ ዘንድ ፡ ከጥፋት ፡ እንድንድንባት ፡ ዘንድ ፡ ይህችን ፡ ምልክት ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ አደረጉ ፡ የግብፃውያንን ፡ በኵር ፡ እንደገደለ ፡ በኵራቸውን ፡ እንዳይገድልባቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ በፋሲካ ፡ የሚታረደውን ፡ የበግ ደም ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ቤት ፡ ቸነፈርን ፡ የሚያርቅ ፡ ምልክት ፡ እንዳደረገው ። በትእምርተ ፡ መስቀል ፡ የሚያማትቡባቸው ፡ ጊዜያቶችም ፡ ጸሎት ፡ ሲጀመር ፡ መስቀልን ፡ ከሚያነሳበት ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፡ ነው ።

፩፻፴፮ አምስተኛውም ፡ በመፍራት ፡ በመንቀጥቀጥ ፡ የጸሎትን ፡ ቃላት ፡ ማንበብ ፡ ነው ፡ የሚነበበውም ፡ ጸሎት ፡ ልብ ፡ ወደ ፡ ፈጣሪ ፡ የሚሳብበት ፡ ይሁን ፡ በአሳብም ፡ ብቻ ፡ ቢሆን ፡ በአንደበትም ፡ ቢሆን ፡ ለሕሊና ፡ ይተረጐም ፡ ዘንድ ።

እንቀጽ ፡ ፲፬ ።

፳፻፴፭ ወሳድስኒ ፡ አስተብርኮ ፡ ወስጊድ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ ጽሑፍ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላክከ ፡ ታምልክ ፡ ወሎቱ ፡ ለባሕቲቱ ፡ ትስግድ ። ወንጌልኒ ፡ ነሰበ ፡ ስምዐ ፡ ይከውን ፡ ዘከመ ፡ ጸለየ ፡ በሌሊተ ፡ ሕማማቲሁ ፡ ወሰገደ ፡ በገጹ ፡ ወአስተብረከ ፡ በብረኪሁ ፡ ወመፍትው ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ስጊዶትነ ፡ በመንፈስ ፡ ወበጽድቅ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ።

፳፻፴፮ ወጊዜያተ ፡ ስጊድሰ ፡ ወኍላቊሁ ፡ ሥሩዕ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንነ ። ወዘይጼሊ ፡ ይስግድ ፡ በዘይበጽሕ ፡ ዝክረ ፡ ስጊድ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ በጊዜ ፡ ጸሎት ፡ ወይውዕዮን ፡ በስጊድ ፡ እሐተ ፡ አው ፡ ፫ተ ፡ ጊዜያተ ፡ ወከማሁ ፡ ይግበር ፡ በተፍጻሜተ ፡ ጸሎቱ ፡ ወያንብብ ፡ መዝሙረ ፡ ወስብሐታተ ። ቦ ፡ እምስብአ ፡ ዘይገብር ፡ መንረቅ ፡ ለውእቱ ፡ ስጊደ ፡ ወመንረቅ ፡ አስተብርኮተ ፡ ወቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘይዌስክ ፡ ላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ በእምጣነ ፡ ኀይሉ ፡ ወጽንዑ ።

፳፻፴፯ ወጊዜያትሰ ፡ እሙራት ፡ ዘየኀድጉ ፡ ባቲ ፡ ስግደተ ፡ እስከ ፡ ምድር ፡ ዘእንበለ ፡ እድንኖ ፡ ወአስተብርኮ ፡ ባቲ ፡ ዛቲ ፡ ይእቲ ። ዘኒቅየ ፡ ፳ ። በሰለተ ፡ እሑድ ፡ ወበመዋዕለ ፡ ጰንጠቈስጤ ፡ ዘኒቅየ ፡ ፶ወ፱ቲ ፡ ወበዓላተ ፡ እግዚእነ ፡ ወበበዓላተ ፡ እግዝእትነ ፡ ወእምድኅረ ፡ ተመጥዎ ፡ ቍርባንኒ ።

፳፻፴፰ ወዘይደሉስ ፡ በጊዜ ፡ ጸሎት ፡ አንሥኦተ ፡ እደዊነ ፡ እንዘ ፡ ስፉሐት ፡ እራኍቲሆን ፡ ወፊድፋደስ ፡ በጊዜ ፡ አስተብቍዖ ፡ በከመ ፡ ይቤሎ ፡ ጳውሎስ ፡ ለጢሞቴዎስ ፡ ዘ፩ቱ ፡ "ወእንበ ፡ እፈቅድ ፡ ከመ ፡ ይጸልዩ ፡ እደው ፡ በኵሉ ፡ መካን ፡ እንዘ ፡ ያነሥኡ ፡ እደዊሆሙ ፡ በንጽሕ ፡ ዘእንበለ ፡ ቍጥዓ ፡ ወኑፋቄ" ። በከመ ፡ ይቤ ፡ ዳዊት ፡ ነቢይ ፡ በ፻፴ወ፫ቱ ፡ "በሌሊት ፡ አንሥኡ ፡ እደዊክሙ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ወባርክዎ ፡ ለእግዚአብሔር" ። ወበእንተ ፡ ብሂሎቱ ፡ በ፻ወ፵ቱ ፡ በ፻፵ወ፩ቱ ፡ አንሥእቱ ፡ እደውየ ፡ ኀቤከ ። ወዓዲ ፡ እንቃዕድዎተ ፡ አዕይንትኒ ፡ መንገለ ፡ ሰማይ ፡ በከመ ፡ ገብረ ፡ እግዚእነ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ አመ ፡ አንሥአ ፡ ለአልአዛር ።

ስለ ፡ ጸሎት ።

፳፻፴፭ ስድስተኛውም ፡ እስተብርኮና ፡ ስግደት ፡ ነው ፡ "እግዚአብሔርን ፡ ልታመልክ ፡ ለርሱም ፡ ብቻ ልትሰግድ ፡ ጽሑፍ ፡ አለ" (ማቴ ፡ ፬ ፡ ፲) ። ብሎ ፡ ጌታችን ፡ እንደተናገረ ። ዳግመኛም ፡ ወንጌል ፡ በመከራው ፡ ሌሊት ፡ እንደጸለየ ፡ (በፊቱ) በግንባሩ ፡ እንደሰገደ ፡ በጉልበቱ ፡ እን ደተንበረከከ ፡ ምስክር ፡ ይሆናል ። ስግደታች ንም ፡ በመንፈስ ፡ በእውነት ፡ መሆን ፡ ይገባ ዋል ። ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባውና ፡ ጌታችን ፡ እንደተናገረ ፡ (ዮሐ ፡ ፬ ፡ ፳፬) ።

፳፻፴፮ የሚሰገድባቸው ፡ ጊዜያቶችና ፡ ቁጥሮች ፡ በቤ ተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ ተጽፈዋል ። የሚጸልይ ፡ ሰው ፡ በጸሎት ፡ ጊዜ ፡ ስግደትን ፡ ከሚያነሣ ፡ እንቀጽ ፡ ሲደርስ ፡ ለልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ይስገድ ፡ በአንድ ፡ ስግደት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ያት ፡ ይጀምር ፡ እንደዚሁም ፡ በጸሎት ፡ መጨረሻ ይስገድ ፡ መዝሙርንና ፡ ምስጋናዎችን ፡ ያን ብብ ። ከሰው ፡ ወገን ፡ እኩሌታውን ፡ ለስግደት ፡ እኩሌታውን ፡ ለአስተብርኮ ፡ የሚያደርግ ፡ አለ ። ከእነዚህም ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ኃይሉና ፡ እንደ ፡ ፅናቱ ፡ መጠን ፡ በዚህ ፡ ላይ ፡ የሚጨ ምር ፡ አለ ።

፳፻፴፯ ከእድንኖና ፡ ከአስተብርኮ ፡ በቀር ፡ እስከ ፡ ምድ ር ፡ መስገድን ፡ የሚተዉባቸውም ፡ የታወቁ ፡ ጊዜያቶች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። ኒቅየ ፡ ፳ ፡ በሰ ለተ ፡ እሑድና ፡ በበዓለ ፡ ሃምሳ ፡ ወራት ፡ ኒቅየ ፡ ፶፱ ፡ በጌታችን ፡ በዓላትና ፡ በእመቤታ ችን ፡ በዓላት ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ከተቀበሉ ፡ በኋላ ።

፳፻፴፰ በጸሎት ፡ ጊዜ ፡ የሚገባውስ ፡ መኽል ፡ እጆች ፡ እንደተበረገ ፡ ሁነው ፡ እጆቻችንን ፡ ማንሣት ፡ ነው ። ይልቁንም ፡ በመማለድ ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስ ፡ ጢሞቴዎስን ፡ እንዳለው ፡ ፩ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ሰዎች ያለ ፡ ቁጣ ፡ ያለ ፡ ጥርጥር ፡ በንጽሕና ፡ እጃቸ ውን ፡ እንሥተው ፡ በቦታው ፡ ሁሉ ፡ እንዲ ጸልዩ ፡ እወዳለሁ ። (፩ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፰)፡ ነቢዩ ፡ ዳዊት ፡ በ፻፴፫ኛው ፡ መዝሙር ፡ እንደተናገረ ፡ በሌሊት ፡ እጃችሁን ፡ አንሥታችሁ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፡ በ፻፵ ኛውና ፡ በ፻፵፩ኛው ፡ መዝሙር ፡ ወደአንተ ፡ እጄን ፡ አነሣሁ ፡ በማለቱ ፡ ዳግመኛም ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባውና ፡ ጌታችን ፡ አልአዛርን ፡ ባስነሣው ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ አደረገ ፡ ዓይኖቻችንን

ወበከመ ፡ ይቤ ፡ ነቢይ ፡ በ፻፳ወ፱ቱ ፡ ኀበከ ፡ እግዚኦ ፡ እንቃዕዶን ፡ አዕይንቲነ ።

፩፻፴፱ ወዘቢጠ ፡ እንግድዓሂ ፡ ጊዜ ፡ አስተሥርዮ ፡ ወንስሐ ። በእንተ ፡ ኀዲግ ፡ እምዕልወታት ፡ ወተከዞ ፡ በእንተ ፡ ዘኀለፈ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ዘእንበለ ፡ ይግበር ፡ ሠናያተ ፡ ከመ ፡ መጸብሐዊ ፡ ዘጐድአ ፡ እንግድዓሁ ፡ በውስተ ፡ ጸሎቱ ፡ ዘተወድሰት ።

፩፻፵ ወብካይኒ ፡ ለዘይትከሀሎ ፡ ከመ ፡ ዳዊት ፡ ወአበው ፡ ቅዱሳን ።

፩፻፵፩ ወዘያነብብዎ ፡ በጊዜ ፡ ጸሎት ፡ ውእቱ ፡ ዘተጽሕፈ ፡ በወንጌል ፡ ወበቀኖና ፡ ፰ ፡ ፲ቱ ፡ ወከመዝ ፡ ጸልዩ ፡ እንትሙሰ ፡ አ ፡ አቡነ ፡ ዘበሰማያት ፡ እስከ ፡ ተፍጻሜቱ ። ዘኒቅያ ፡ ወይበሉ ፡ ጸሎተ ፡ ሃይማኖት ፡ በኵሉ ፡ ተፍጻሜተ ፡ ጸሎት ።

፩፻፵፪ ረስጣ ፡ ፳ወ፱ቱ ፡ ወይኩን ፡ ፍድፋዴ ፡ ጸሎት ፡ በኵሉ ፡ ዕለት ፡ ሌሊተ ፡ ወመዓልተ ፡ እመዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ በእንተ ፡ ዘሀሎ ፡ ውስቴቱ ፡ እእኵቶ ፡ ወስብሖ ፡ ወእስተብቍዖ ፡ ወነቢበ ፡ ከዊኖቱ ፡ ፩ደ ፡ ለፈጣሪ ፡ ወተእምኖ ፡ ኀጣውእ ።

፩፻፵፫ ድስቅ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ወያንብቡ ፡ በጸሎተ ፡ ነግህ ፡ መዝሙረ ፡ ዘ፷ወ፪ቱ ፡ ወበሠርከኒ ፡ መዝሙረ ፡ ዘ፻ወ፴ ።

፩፻፵፬ ዶቅ ፡ ፲ወ፬ቱ ፡ ወይጸልዩ ፡ ካህናት ፡ በኵሉ ፡ ዕለት ፡ ሰብሐተ ፡ ፫ቱ ፡ ደቂቅ ፡ ወይኅትሙ ፡ ጸሎቶሙ ፡ ለዓለም ፡ በጸሎተ ፡ እግዝእትነ ፡ ማርያም ። ወበዕለተ ፡ ሰኑይሰ ፡ ይጸልዩ ፡ ካዕበ ፡ በሰብሐተ ፡ ሙሴ ፡ ወእኅቱ ፡ እመ ፡ ወዕአ ፡ እምባሕር ፡ ሶበ ፡ አድኀኖሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ። ወበዕለተ ፡ ሠሉስ ፡ ስብሐተ ፡ ዳግም ፡ ሕግ ፡ ዘአሪት ። ወበዕለተ ፡ ረቡዕ ፡ ጸሎተ ፡ ሐና ፡ እመ ፡ ሳሙኤል ። ወበዕለተ ፡ ሐሙስ ፡ ጸሎተ ፡ እንባቆም ፡ ነቢይ ። ወበዕለተ ፡ ዓርብ ፡ ጸሎተ ፡ ኢሳይያስ ፡ ነቢይ ። ወበዕለተ ፡ ሰንበት ፡ ጸሎተ ፡ ዮናስ ፡ ነቢይ ። ወበዕለተ ፡ እሑድ ፡ ይጸልዩ ፡ ዘንተ ፡ ኵሎ ፡ ጸሎታተ ፡ ዘእቅድምነ ፡ ዘከሮቶሙ ። ወናሁ ፡ ሠርዑ ፡ አበው ፡ ጸሎታተ ፡ ዘይትዌሰክ ፡ ላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ ወካልእኒሁ ፡ ወይደሉ ፡ ይጸልዩ ፡ በሙ ።

፩፻፵፭ ድስቅ ፡ ፴ወ፯ቱ ፡ ረስጣ ፡ ፵ ፡ ረስጠጅ ፡ ፳ቱ ፡



ወደሰማይ ፡ ማቅናት ፡ ነው ። (ዮሐ ፡ ፲፯ ፡ ፵፩) ። ነቢዩ ፡ ዳዊት ፡ በ፻፳፱ኛው ፡ መዝሙር ፡ አቤቱ ፡ ዓይኖቻችንን ፡ ወደአንተ ፡ አቀናን ፡ እንዳለ ።

፩፻፴፱ ከኀጢአት ፡ ለመለየት ፡ በአስተሥርዮና ፡ በንስሓ ፡ ጊዜ ፡ ደረትን ፡ መድቃት ፡ ነው ፡ በጎ ፡ ሳይሠራ ፡ ዘመኑ ፡ ስላለፈ ፡ ማዘን ፡ ነው ፡ በተመስገኘ ፡ ጸሎቱ ፡ ደረቱን ፡ እንደ ፡ ደቃው ፡ መጸብሐዊ ፡ (ሉቃ ፡ ፲፰ ፡ ፲፫) ።

፩፻፵ ለሚቻለው ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ እንደ ፡ ቅዱሳን ፡ አባቶች ፡ ማልቀስ ፡ ነው ።

፩፻፵፩ በጸሎት ፡ ጊዜ ፡ የሚያነቡት ፡ በወንጌልና ፡ በመጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ ነው ። ፰ ፡ ፲ ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ድረስ ፡ በሰማይ ፡ የምትኖር ፡ አባታችን ፡ ሆይ ፡ ብላችሁ ፡ እንደ ፡ ዚህ ፡ ጸልዩ ። ኒቅያ ፡ በጸሎቱ ፡ መጨረሻ ፡ ሁሉ ፡ ጸሎተ ፡ ሃይማኖትን ፡ ይበሉ ።

፩፻፵፪ ረስጣ ፡ ፳፱ ፡ በመዓልትና ፡ በሌሊት ፡ ሁሉ ፡ የሚጸለየው ፡ ጸሎት ፡ ከዳዊት ፡ መዝሙር ፡ ይሁን ፡ በውስጡ ፡ ምስጋና ፡ መማለድ ፡ የፈጣሪን ፡ አንድነቱን ፡ መናገር ፡ ኃጢአትን ፡ ማመን ፡ ስላለበት ።

፩፻፵፫ ድስቅ ፡ ፲፪ ፡ በማለዳው ፡ ጸሎት ፡ ፷፪ኛውን ፡ መዝሙር ፡ በማታውም ፡ ጸሎት ፡ ፻፵ኛውን ፡ ይጸልዩ ።

፩፻፵፬ ዶቅ ፡ ፲፬ ፡ ካህናት ፡ ዘወትር ፡ የሠለስቱ ፡ ደቂቅን ፡ ምስጋና ፡ ይጸልዩ ፡ ጸሎታቸውንም ፡ በጸሎተ ፡ እግዚእትነ ፡ ማርያም ፡ ይጨርሱ ። ዳግመኛም ፡ በሰኞ ፡ ቀን ፡ የሙሴንና ፡ የእኅቱን ፡ ምስጋና ፡ ይጸልዩ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ከባሕር ፡ አድኖ ፡ ባወጣቸው ፡ ጊዜ ፡ ማክሰኞ ፡ ቀን ፡ ከኦሪት ፡ የተገኘውን ፡ ሁለተኛውን ፡ ሕግ ፡ ይጸልዩ ፡ ረቡዕ ፡ ቀን ፡ የሳሙኤልን ፡ እናት ፡ የሐናን ፡ ጸሎት ፡ ይጸልዩ ። ሐሙስ ፡ ቀን ፡ የነቢዩ ፡ የዕንባቆምን ፡ ጸሎት ፡ ይጸልዩ ። ዓርብ ፡ ቀን ፡ የነቢዩን ፡ የኢሳይያስን ፡ ጸሎት ፡ ይጸልዩ ። ቅዳሜ ፡ የነቢዩ ፡ የዮናስን ፡ ጸሎት ፡ ይጸልዩ ። በዕለተ ፡ እሑድ ፡ ግን ፡ አስቀድመን ፡ የተናገርናቸውን ፡ ጸሎቶች ፡ ሁሉ ፡ ይጸልዩ ። እነሆ ፡ አባቶች ፡ በዚህና ፡ በሌላውም ፡ ላይ ፡ የሚጨመር ፡ ጸሎት ፡ ሠሩ ። በእነዚያ ፡ ሊጸልዩ ፡ ባቸው ፡ ይገባል ።

፩፻፵፭ ድስቅ ፡ ፴፯ ፡ ረስጣ ፡ ፵ ፡ ረስጠጅ ፡ ፳ ፡ በደስ ፡

በደስ ፡ ፳ወ፫ቱ ፡ ፳ወ፭ቱ ፡ በስ ፡ ፳ወ፰ቱ ፡ ወጸሎትስ ፡ ዘተአዘዘ ፡ ላዕለ ፡ ኵሎሙ ፡ ምእመናን ፡ በኵሉ ፡ ዕለት ፡ ፯ቱ ፡ ጊዜያት ። ቀዳሚሁ ፡ እምቅድመ ፡ ሥርቀተ ፡ ፀሐይ ፡ በጊዜ ፡ ንቅሖሙ ፡ ወተንሥኦሙ ፡ በነግህ ፡ እምስካቦሙ ። ወይደሉ ፡ ጸሎት ፡ እምድኅረ ፡ ተሐፅቦ ፡ እደዊሆሙ ፡ በማይ ፡ ይጸልዩ ፡ ቅድመ ፡ ተገብሮ ፡ ግብር ። ወዳግምኒ ፡ ጸሎተ ፡ ፫ቱ ፡ ሰዓት ፡ ወሣልስኒ ፡ ጸሎተ ፡ ፮ቱ ፡ ሰዓት ። ወራብዕኒ ፡ ጸሎተ ፡ ፱ቱ ፡ ሰዓት ፡ ወኃምስኒ ፡ ጸሎተ ፡ ሠርክ ። ወሳድስኒ ፡ ጸሎተ ፡ ንዋም ። ወሳብዕኒ ፡ ጸሎተ ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ እምድኅረ ፡ ተሐፅቦ ፡ እደዊሆሙ ፡ በማይ ፡ ወለእመ ፡ ኢረከቡ ፡ ማየ ፡ በውእቱ ፡ ጊዜ ፡ ይንፍሑ ፡ እደዊሆሙ ፡ ወይዕትቡ ፡ በምራቅ ፡ ዘይወፅእ ፡ እምአፉሆሙ ።

፳፫ ፡ ፳፭ ፡ በስ ፡ ፳፰ ፡ ዘወትር ፡ ለምእመናን ፡ ሁሉ ፡ የታዘዘው ፡ ጸሎት ፡ ግን ፡ በ፯ቱ ፡ ጊዜያቶች ፡ ነው ፡ መጀመሪያው ፡ ፀሐይ ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ በንቁ ፡ ጊዜ ፡ ከመኝታቸው ፡ ተንሥተው ፡ በማለዳ ፡ ነው ። እጃቸውን ፡ በውኃ ፡ ከታጠቡ ፡ በኋላ ፡ ሥራ ፡ ከመሥራት ፡ በፊት ፡ ጸሎት ፡ መጸለይ ፡ ይገባል ። ሁለተኛም ፡ የሦስት ፡ ሰዓት ፡ ጸሎት ፡ ነው ። ሦስተኛውም ፡ የስድስት ፡ ሰዓት ፡ ጸሎት ፡ ነው ። አራተኛውም የ፱ ፡ ሰዓት ፡ ጸሎት ፡ ነው ። አምስተኛውም ፡ የ፲፪ኛው ፡ ሰዓት ፡ ጸሎት ፡ ነው ። ስድስተኛውም የመኝታ ፡ ጊዜ ፡ ጸሎት ፡ ነው ፡ ሰባተኛውም ፡ እጃቸውን ፡ ከታጠቡ ፡ በኋላ ፡ የሚጸልዩት ፡ የመንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ ጸሎት ፡ ነው ። በዚያም ፡ ጊዜ ፡ ውኃ ፡ ባያገኙ ፡ እፍ ፡ ብለው ፡ ከአፋቸው፡ በሚወጣው ፡ ምራቅ ፡ ታጥበው ፡ ያማትቡ ።

፳፻፵፮ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ምስለ ፡ ብእሲቱ ፡ ፪ሆሙ ፡ ይጸልዩ ፡ ኅቡረ ፡ ወእመሰ ፡ ኮነት ፡ ዘኢ.ተእምን ፡ ይትፈለጥ ፡ ወይጸሊ ፡ ባሕቲቱ ፡ ወኢይዴኀሩ ፡ እምጸሎት ፡ እለ ፡ እሡራን ፡ በሰብሳብ ፡ ወኢይኅሥሡ ፡ ተሐፅቦ ፡ በቤተ ፡ ብስኤ ፡ እንበለ ፡ ተሐፅቦ ፡ እድ ፡ ባሕቲቱ ፡ እስመ ፡ ሰብሳቦሙ ፡ ንጹሕ ፡ ውእቱ ። ወበእንተሰ ፡ ዘተሠርዑ ፡ ፯ቱ ፡ ጊዜያት ፡ ናሁ ፡ ይቤ ፡ ዳዊት ፡ "ስብዐ ፡ ለዕለትየ ፡ እሴብሐከ ፡ አ ፡ እግዚኦ" ።

፳፻፵፮ ከሚስቱ ፡ ጋር ፡ ቢሆን ፡ ሁለቱም ፡ በአንድነት፡ ይጸልዩ ፡ ያላመነች ፡ ብትሆን ፡ ግን ፡ ተለይቶ ፡ ብቻውን ፡ ይጸልይ ፡ በጋብቻ ፡ አንድ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ በጸሎት ፡ አይለያዩ ፡ እጃቸውን ፡ ከመታጠብ ፡ በቀር ፡ በፍል ፡ ውኃ ፡ መታጠብን ፡ አይፈልጉ ። ጋብቻቸው ፡ (ሩካቤያቸው) ፡ ንጹሕ ነውና ። በሰባቱ ፡ ጊዜያቶች ፡ ስለተሠሩ ፡ ጸሎቶች ፡ ግን ፡ እነሆ ፡ ዳዊት ፡ "እቤቱ ፡ በየዕለቱ ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ አመሰግንሃለሁ ፡ አለ ።" (መዝ ፡ ፻፲፰ ፡ ፻፷፬) ።

፳፻፵፯ ረስጣ ፡ ፳ወ፰ቱ ፡ ወጸሎተ ፡ ነግህሰ ፡ እስመ ፡ እግዚእብሔር ፡ አብርሀ ፡ ለነ ፡ ወአኅለፈ ፡ ለጽልመተ ፡ ሌሊት ። ወበ፫ቱ ፡ ሰዓት ፡ በእንተ ፡ ዘፈትሐ ፡ ባቲ ፡ ጲላጦስ ፡ ላዕለ ፡ እግዚእነ ። ወበስድስቱ ፡ ሰዓት ፡ ተሰቅለ ። ወበጊዜ ፡ ተስዓቱኒ ፡ ሰዓት ፡ መጠወ ፡ ነፍሶ ። ወበሌሊትኒ ፡ እእኵትዎ ፡ ለእግዚእብሔር ፡ በእንተ ፡ ዘወሀበነ ፡ ዕረፍተ ፡ እምጻማ ፡ መዓልት ። ወሰብሕዎ ፡ ለእግዚእብሔር ፡ በእሎን ፡ ጊዜያት ፡ እስመ ፡ ተወክፈ ፡ በእንቲእነ ፡ ሕማማተ ፡ ወስቅለተ ፡ ወሰትየ ፡ ሐሞት ፡ መሪረ ፡ ወሞተ ፡ ወረደ ፡ ውስተ ፡ መቃብር ፡ በጊዜ ፡ ዕርበተ ፡ ፀሐይ ። ወበመንፈቀ ፡ ሌሊትኒ ፡ ይመጽእ ፡ መርዓዊ ፡ ቦቱ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ዳዊት ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ እትነሣእ ፡ ከመ ፡ እግነይ ፡ ለከ ፡ ወቦቱ ፡ ኮኑ ፡ ይጼልዩ ፡ ጳውሎስ ፡ ወሲላስ ፡ ኀበ ፡ እግዚእብሔር ፡ በውስተ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ። ወእግዚእነሂ ፡ ጸለየ ፡ በሌሊተ ፡ ሕማማቲሁ ፡ ፫ተ ፡ ጊዜያተ ፡

፳፻፵፯ ረስጣ ፡ ፳፰ ፡ የማለዳው ፡ ጸሎት ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ አብርቶልናልና ፡ የሌሊቱንም ፡ ጨለማ ፡ አሳልፎልናልና ፡ ስለዚህ ፡ ነው ። በ፫ ሰዓት ፡ መጸለይም ፡ ጲላጦስ ፡ በጌታችን ፡ ላይ ፡ ስለፈረደበት ፡ ነው ። በ፮ ፡ ሰዓትም ፡ ስለተሰቀለ ፡ ነው ፡ በ፱ም ፡ ሰዓት ፡ ነፍሱን ፡ ከሥጋው ፡ ስለለየ ፡ ነው ። በሌሊትም ፡ (በንዋም) ጊዜ ፡ ከቀኑ ፡ ድካም ፡ አሳርፎ ፡ ዕረፍትን ፡ ስለሰጣችሁ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑት ፡ በእነዚህ ፡ ጊዜያቶች ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑት ፡ ስለእኛ ፡ መከራን ፡ ስቅለትን ፡ መራራ ፡ ሐሞት ፡ መጠጣትን ፡ ሞትን ፡ ፀሐይ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ወደመቃብር ፡ መውረድን ፡ ተቀብሏልና ። በመንፈቀ ፡ ሌሊትም ፡ ሙሽራው ፡ ይመጣበታልና ፡ "አመስግንህ ፡ ዘንድ ፡ በመንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ እነሣለሁ ፡ ብሎ ፡ ዳዊት ፡ እንደ ተናገረ" (መዝ ፡ ፻፲፰ ፡ ፷፪) ጳውሎስና ፡ ሲላ

ወይቤ ፡ "ትግሁ ፡ ወጸልዩ ፡ ከመ ፡ ኢትባኡ ፡ ውስተ ፡ መንሱት" ። ወይቤ ፡ ካዕበ ፡ ተዐቀቡ ፡ እስመ ፡ ኢተአምሩ ፡ እንትሙ ፡ 'ጊዜ ፡ ይመጽእ ፡ ወልደ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ እመሂ ፡ ሠርከ ፡ ወእመሂ ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ ወእመሂ ፡ ጊዜ ፡ ይነቁ ፡ ዶርሆ ፡ ወእመሂ ፡ ጸቢሐ" ።

፩፻፵፰ ረስጣ ፡ ፵ወ፰ቱ ፡ ድስቅ ፡ ፲ወ፱ቱ ፡ ወይኩን ፡ ጸሎተ ፡ ነግህ ፡ ወሰርክ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወፈድፋደሰ ፡ በሰለተ ፡ እሑድ ፡ ወሰንበት ፡ ወዘተድኅረ ፡ ዘእንበለ ፡ ደዌ ፡ ይትፈለጥ ፡ ወእመ ፡ ተክህሎ ፡ ለድዉይ ፡ ለበጺሕ ፡ ኢይደኅር ፡ ከመ ፡ ይርከብ ፡ ፈውሰ ፡ በዘይነሥእ ፡ እማየ ፡ ጸሎት ፡ ወዘይት ፡ ወእመሰ ፡ ኮነ ፡ ድዉየ ፡ ዘኢይክል ፡ መጺአ ፡ ለየሐውጽዎ ፡ ማእምራኒሁ ፡ ኵሎ ፡ ሰለተ ።

፩፻፵፱ ረስጠብ ፡ ፵ወ፺ቱ ፡ ወጸሎተ ፡ ፫ቱ ፡ ሰዓት ፡ ወዘድኅሬሁ ፡ ይደሉ ፡ ይጸልዩ ፡ ውስተ ፡ ቤት ። ወሶበ ፡ በጽሐ ፡ ጊዜ ፡ ጸልዮ ፡ በእሐቲ ፡ እምእሎን ፡ ጊዜያት ፡ ወምእመን ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ኀበ ፡ ዘኢያትክሀሎ ፡ መካን ፡ ለጸልዮ ፡ ይጸሊ ፡ በልብ ። ወጸሎትሰ ፡ ዘይደልዎሙ ፡ ለካህናት ፡ ባሕቲቶሙ ፡ ሥሩስ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጸሎተ ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ ወጸሎተ ፡ ቅዳሴ ፡ ቍርባን ፡ ወጸሎተ ፡ ሢመተ ፡ ክህነት ፡ ወቅዳሴ ፡ ታቦት ፡ ወቅዳሴ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወጸሎተ ፡ ሰብሳብ ፡ ወፍትሐት ፡ ወጸሎተ ፡ ፈውስ ፡ ለድዉያን ፡ ወጸሎተ ፡ ሙታን ፡ ጊዜ ፡ ፍልሰቶሙ ፡ ወእምድኅሬሃ ።

፩፻፶ በደስ ፡ ፫ቱ ፡ ወጸሎተ ፡ ዘይት ፡ ወበኵረ ፡ መብልዕ ፡ ወኵሉ ፡ ጸሎት ፡ እንተ ፡ ትትበሀል ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡ ግብር ፡ ይበሉ ፡ በተፍጻሜተ ፡ ጸሎት ፡ ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እስከ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ። ወጸሎተ ፡ ጥምቀትኒ ፡ ወንብተራ ፡ በከመ ፡ ተዘክረ ፡ ውስተ ፡ ወንጌል ፡ ወይእቲ ፡ ዘወዕአት ፡ እመጽሐፈ ፡ ቅዳሴ ።

፩፻፶፩ ወጸሎታትስ ፡ ዘኢተሠርዓ ፡ ጸሎተ ፡ ተፀምዶ ፡ ዘመነኰሳት ፡ ወፈራዚያን ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ይጼልዩ ፡ ፈድፋደ ፡ ሌሊተ ፡ ወመዓልተ ፡



ስም ፡ በእሥር ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጸልዩበት ፡ ነበር ። ጌታችንም ፡ በመከራው ፡ ሌሊት ፡ ፫ ፡ ጊዜ ፡ ጸለየ ፡ ወደፈተና ፡ እንዳትገቡ ፡ ተግታችሁ ፡ ጸልዩ ፡ አለ" (ማቴ ፡ ፳፮ ፡ ፵፩) ። ዳግመኛም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ የሚመጣበትን ፡ ጊዜ ፡ ማታም ፡ ቢሆን ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊትም ፡ ቢሆን ፡ ዶሮ ፡ ሲጮህም ፡ ቢሆን ፡ ሲነጋም ፡ ቢሆን ፡ አታውቁምና ፡ ተጠበቁ ፡ አለ ፡ (ማር ፡ ፲፫ ፡ ፴፭-፴፯) ።

፩፻፵፰ ረስጣ ፡ ፵፰ ፡ ድስቅ ፡ ፲፱ ፡ የጥዋትና ፡ የማታ ፡ ጸሎት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ይሁን ፡ ይልቁንም ፡ በቅዳሜና ፡ በእሑድ ፡ ቀን ፡ ደዌ ፡ ሳያገኘው ፡ ወደኋላ ፡ ያለ ፡ ይለይ ፡ ሕመምተኛው ፡ መምጣት ፡ ቢቻለው ፡ እየዘገየ ፡ ከቅዳሴው ፡ ጠበል ፡ ጠጥቶ ፡ ከዘይቱ ፡ ተቀብቶ ፡ ድኅነትን ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡ መምጣት ፡ የማይቻለው ፡ ሕመምተኛ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ የሚያውቁት ፡ ዘወትር ፡ ይጠይቁት ።

፩፻፵፱ ረስጠብ ፡ ፵፺ ፡ የሦስቱን ፡ ሰዓትና ፡ ከእርሱ ፡ በኋላ ፡ (ቀጥሎ) ፡ ያለውን ፡ የሰዓት ፡ ጸሎት ፡ በቤት ፡ መጸለይ ፡ ይገባል ። ከእነዚህ ፡ ጊዜያቶች ፡ በአንዲቱ ፡ የመጸለያው ፡ ጊዜ ፡ ቢደርስ ፡ ምእመንም ፡ ለመጸለይ ፡ ከማይችልበት ፡ ቦታ ፡ ቢሆን ፡ በልቡ ፡ ይጸልይ ፡ (ያስብ) ፡ ካህናት ፡ ብቻቸውን ፡ ሊጸልዩት ፡ የሚገባቸው ፡ ጸሎት ፡ ግን ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተጽፏል ። የክርስትና ፡ ጥምቀት ፡ ጸሎት ፡ የቅዳሴ ፡ ጸሎት ፡ የክህነት ፡ ሹመት ፡ ጸሎት ፡ ታቦት ፡ ሲባረክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሲባረክ ፡ የኀብረ ፡ ጸሎት ፡ ጸሎተ ፡ ቡራኬ ፡ የሕመምተኞች ፡ ድኅነት ፡ ጸሎት ፡ በሞቱ ፡ ጊዜና ፡ ከሞታቸው ፡ በኋላ ፡ የሙታን ፡ ጸሎት ፡ አለ ።

፩፻፶ በደስ ፡ ፫ ፡ የሚሮን ፡ ጸሎት ፡ የበኵራት ፡ ጸሎት ፡ ስለ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ የምትጸለየውን ፡ ጸሎት ፡ ሁሉ ፡ በጸሎቱ ፡ መጨረሻ ፡ ለአብና ፡ ለወልድ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ምስጋና ፡ ይገባል ፡ ይበሉ ፡ እስከ ፡ ዘለዓለሙ ፡ ድረስ ፡ አሜን ። በወንጌል ፡ እንደተነገረ ፡ የጥምቀትና ፡ የጸሎተ ፡ ሐሙስ ፡ ጸሎት ፡ ይህችውም ፡ ከቅዳሴ ፡ መጽሐፍ ፡ የተውጣጣች ፡ ናት ።

፩፻፶፩ ጊዜ ፡ ያልተወሰነባቸው ፡ ጸሎቶች ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈሩ ፡ የመነኰሳት ፡ አገልግሎት ፡ ጸሎት ፡ ነው ። ከነርሱ ፡ ፈጽመው ፡ ቀንም ፡

በከመ ፡ ተነግረ ፡ አምሳሊሁ ፡ ወአምሳላት ፡
እግዚአብሔርት ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ሐዋርያ ፡ ጸልዩ ፡
ዘእንበለ ፡ ዕርዓት ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ኩኑ ፡ ለጸ
ሎት ፡ መዘለፍያን ። ወእሙንቱ ፡ እንዘ ፡ ይኄል
ቍዎ ፡ በጸሎተ ፡ ንግህ ፡ ጊዜ ፡ ንቅወተ ፡ ዶርሆ፡
ምስለ ፡ ሥሩዓት ፡ በከመ ፡ ነገረ ፡ ተናገት ።

፩፻፶፪ ረስጠብ ፡ ፃወጊተ ፡ በስ ፡ ጽወጽተ ፡ በዶስ ፡
ጽወፅዱ ፡ ይቤ ፡ ዳዊት ፡ በሃወጊተ ፡ በጽባሕ ፡
አትነግእ ፡ ወአትአመን ፡ ብከ ። ወእምዝ ፡
ጸሎተ ፡ ማእደ ፡ ቅድሜሁ ፡ ወድኅሬሁ ።

፩፻፶፫ በስ ፡ ጽወጽተ ፡ ወእምቅድሜሁስ ፡ ከመ ፡ ይባ
ርክ ፡ እግዚአብሔር ፡ መባልዕተ ፡ ዘይትበልዑ ፡
ወድኅሬሁኒ ፡ ከመ ፡ ይረስዮ ፡ እግዚአብሔር ፡
ስቅበተ ፡ ለሥጋ ፡ ወለጥዒና ፡ ወይጽንዑ ፡ ለተ
ፀምዶት ፡ እንተ ፡ ትትገበር ። ወነዋ ፡ ኮኑ ፡ ካህ
ናት ፡ ይጼልዩ ፡ ባቲ ፡ ምስለ ፡ ሕዝብ ፡ ወእሙ
ንቱ ፡ ንቡራን ፡ በከመ ፡ ገብረ ፡ እግዚእነ ፡ ሶበ ፡
ነጸረ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡ ወባረከ ፡ ላዕለ ፡ ኃምስ ፡
ኅብስት ።

፩፻፶፬ ወእምዝ ፡ ጸሎተ ፡ ነጊደ ፡ ከመ ፡ ጸለየ ፡ ጳው
ሎስ ፡ እመ ፡ አስተፋነውዎ ፡ ሰብአ ፡ ኤፌሶን ፡
ወጊዜ ፡ ነገደ ፡ እምሚሮስ ፡ እስከ ፡ ኀበ ፡ አካ
ይያ ።

፩፻፶፭ ወእምዝ ፡ ጸሎት ፡ እንተ ፡ አኀጸርዋ ፡ ወረሰይዋ፡
መነኮሳት ፡ ሶበ ፡ ይበውኡ ፡ ውስተ ፡ ቤቶሙ ፡
ወጊዜ ፡ ይወፅኡ ፡ እምኔሁ ።

፩፻፶፮ ወእምገዝኒ ፡ ጸሎት ፡ ዘመፍቅድ ፡ ላቲ ፡ ለአእ
ትቶ ፡ ምንዳቤ ፡ ወያእቲ ፡ ፱ቱ ፡ አክፋል ። ወጸ
ሎተ ፡ ብእሲስ ፡ በእንተ ፡ ነፍሱ ፡ ዝኒ ፡ በእንተ ፡
ቃለ ፡ ሐዋርያ ፡ እመቦ ፡ ፅዱ ፡ እምኔከሙ ፡
ዘሀሎ ፡ ውስተ ፡ ምንዳቤ ፡ ለይጸሊ ። ወጳውሎስ
ወዮናስኒ ፡ ወ፫ቱ ፡ ደቂቅኒ ፡ ጸለዩ ፡ በምንዳቤ
ሆሙ ፡ ወድኅኑ ፡ ወእግዚእነኒ ፡ መሀረነ ፡ ዘንተ
በጸሎቱ ፡ ዘሌሊተ ፡ ሕማሙ ። ወጸሎተ ፡ ካልእ
ኒሁስ ፡ በእንቲአሁ ፡ ግብረ ፡ ሐዋርያት ፡ ስምዐ፡
ኮነ ፡ ከመ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ኮነት ፡ ትጼሊ ፡
በእንተ ፡ ጴጥሮስ ፡ አመ ፡ ኮነ ፡ ሙቁሐ ። ወጳው
ሎስኒ ፡ ይቤ ፡ ጸልዩ ፡ በእንቲአየ ፡ ከመ ፡ እድ
ኅን ።

፩፻፶፯ ወእምዝ ፡ ጸሎተ ፡ ሥርየት ፡ በእንተ ፡ አበሳ ፡

ሌሊትም ፡ ይጸልያሉና ፡ በባህል ፡ በልማድ ፡
በሕግ ፡ እንደተነገረ ፡ ሐዋርያው ፡ "ሳታቋርጡ፡
ጸለዩ" (፩ኛ ፡ ተሰ ፡ ፭ ፡ ፲፯) ። እንዳለ ፡ ዳግመ
ኛም ፡ "ጸሎትን ፡ የምታዘወትሩ ፡ ሁኑ ፡ አለ"
(ቆላ ፡ ፬ ፡ ፪) ። እነርሱም ፡ ከታዘዙት ፡ ጋር ፡
ዶሮ ፡ በሚጮኽ ፡ ጊዜ ፡ ከጠዋቱ ፡ ጸሎት ፡ ሲቆጥ
ሩት ፡ ነው ፡ መጽሐፉ ፡ እንደተናገረ ።

፩፻፶፪ ረስጠብ ፡ ፃጊ ፡ በስ ፡ ጽጽ ፡ በዶስ ፡ ጽፅ ፡ ዳዊት ፡
በሃጊተኛው ፡ መዘሙር ፡ በማለዳ ፡ እነግለሁ ፡
በአንተም ፡ አምናለሁ ፡ ብሎ ፡ እንደተናገረ ።
ከዚህም ፡ ከመብላት ፡ በፊትና ፡ ከመብላት ፡
በኋላ ፡ የሚጸለይ ፡ የምግብ ፡ ጸሎት ፡ ነው ።

፩፻፶፫ በስ ፡ ጽጽ ፡ መጀመሪያ ፡ ግን ፡ የሚበሉትን ፡
ምግቦች ፡ እግዚአብሔር ፡ ይባርክ ፡ ዘንድ ፡ በመ
ጨረሻም ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰውነትን ፡ የሚጠ
ብቅ ፡ ለድኅነት ፡ ያደርገው ፡ ዘንድ ፡ ለምትሠ
ራውም ፡ አገልግሎት ፡ ይጸኑ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።
እነሆ ፡ ካህናት ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋር ፡ ይጸልዩባታል።
እነርሱም ፡ ተቀምጠው ፡ ሳለ ፡ ጌታችን ፡ ወደ
ሰማይ ፡ ተመልክቶ ፡ አምስቱን ፡ ኅብስት ፡
እንደባረከ ።

፩፻፶፬ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የመንገድ ፡ ጸሎት ፡ ነው ፡ ጳው
ሎስ ፡ የኤፌሶን ፡ ሰዎች ፡ በሸኙት ፡ ጊዜ ፡ ከሚ
ሮስም ፡ ወደአካይያ ፡ በሄደ ፡ ጊዜ ፡ እንደጸለየ ።

፩፻፶፭ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ መነኮሳት ፡ ያሳጠሯትና ፡ የወ
ሰኗት ፡ ጸሎት ፡ ናት ፡ ወደቤታቸው ፡ በገቡ ፡
ጊዜ ፡ ከቤታቸውም ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ።

፩፻፶፮ ከዚህም ፡ ቀጥሎ ፡ መከራን ፡ ለማራቅ ፡ የፈቃድ
ጸሎት ፡ ነው ፡ ይህችውም ፡ ፱ ፡ ክፍል ፡ ናት ፡
ሰው ፡ ስለራሱ ፡ የሚጸልያት ፡ ጸሎት ፡ ናት ፡
ይኸውም ፡ ሐዋርያው ፡ ከእናንተ ፡ ወገን ፡
አንዱ ፡ ሰው ፡ በመከራ ፡ ያለ ፡ ቢሆን ፡ ይጸልይ፡
ስላለ ፡ ነው ። (ያዕ ፡ ፭ ፡ ፲፫) ጳውሎስ ፡ ዮናስ ፡
፫ ፡ ደቂቅም ፡ በመከራቸው ፡ ጸለዩ ፡ ዳኑም ፡ ጌታ
ችንም ፡ መከራ ፡ በተቀበለበት ፡ ሌሊት ፡ ይህን ፡
ጸሎቱን ፡ አስተማረን ፡ የባልንጀራ ፡ ጸሎት ፡
ግን ፡ ስለርሱ ፡ የሐዋርያት ፡ ሥራ ፡ ምስክር ፡
ሆነ ፡ በታሠረ ፡ ጊዜ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለ ፡
ጴጥሮስ ፡ ትጸልይ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ (የሐዋ ፡ ፲፪ ፡
፭) ጳውሎስም ፡ "እድን ፡ ዘንድ ፡ ስለእኔ ፡
ጸልዩ" አለ ። (ኤፌ ፡ ፮ ፡ ፲፱)

፩፻፶፯ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ስለበደል ፡ የሚጸለይ ፡ የን

ከመ ፡ ጸሎተ ፡ ካህን ፡ በእንተ ፡ ሕዝብ ፡ በከመ ፡ ገብሩ ፡ ሙሴ ፡ ወአሮን ፡ ወፊንሐስ ።

፩፻፶፰ ወእምዝ ፡ ጸሎተ ፡ መፍቅድ ፡ ዘባቲ ፡ ትትፌጸም ፡ መፍቅድ ፡ እንተ ፡ ኢትከልእ ፡ እምኔሃ ፡ ሕግ ፡ ከመ ፡ ኀሚሠ ፡ ዘርእ ፡ ውኅሚሠ ፡ ጥበብ ፡ ከመ ፡ ጸሎተ ፡ ሐና ፡ እንተ ፡ ተጸገወት ፡ ባቲ ፡ ሳሙኤልሃ ፡ ወስብሐታኒ ፡ ሶበ ፡ ወሰደቶ ። ወበከመ ፡ ባህሉ ፡ ለሐዋርያ ፡ እመቦ ፡ ዘንጥእ ፡ ለጥበብ ፡ ለይስአል ፡ ኀበ ፡ ወሃቢ ፡ እግዚአብሔር ፡ በስፉሕ ፡ ወኢይናፍቅ ፡ ቦቱ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይሁቦ ፡ ለዘሰአለ ፡ ወከመ ፡ ባህሉ ፡ ለእግዚእነ ፡ ወኵሉ ፡ ዘትሰእሉ ፡ ውስተ ፡ ጸሎት ፡ በሃይማኖት ፡ ትነሥኡ ።

፩፻፶፱ ወእምዝ ፡ ጸሎተ ፡ እበው ፡ መንፈሳውያን ፡ በእንተ ፡ ውሉዶሙ ፡ በከመ ፡ ጸሎተ ፡ ጳውሎስ ፡ ወእዝዞቱ ፡ ለረድኡ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ በዝንቱ ።

፩፻፷ ረስጠጅ ፡ ፵ወ፫ቱ ፡ ድስቅ ፡ ፴ወ፫ቱ ፡ ወኢይደሉ ፡ ጸሎት ፡ ምስለ ፡ ካህን ፡ ውጉዝ ። ወኢምስለ ፡ ዘኢየአምን ፡ ወእመኒ ፡ ኮነ ፡ ውስተ ፡ ቤት ፡ ወዘጸለየ ፡ ምስለ ፡ እሉ ፡ ይትመተር ።

፩፻፷፩ ድስቅ ፡ ፰ቱ ፡ ወይደልወክሙ ፡ እ ፡ አኀዊነ ፡ ከመ ፡ ትጸልዩ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ ከመ ፡ ይትመየጡ ፡ መዝለፍያነ ፡ መዓት ፡ እንበለ ፡ ርትዕ ፡ ኀበ ፡ ኀዲገ ፡ ቍጥዓ ።

፩፻፷፪ ዘ፲ቱ ፡ ወሶበ ፡ ቦአ ፡ እንግዳ ፡ ክቡር ፡ ወበኀለ ፡ ሀገር ፡ ኢትምትር ፡ ነገረከ ፡ እ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዳእሙ ፡ ይትወከፍዎ ፡ አኃው ፡ ኀቤሆሙ ፡ ወያርኅብ ፡ ሎቱ ፡ ዲያቆን ፡ መካነ ፡ ከመ ፡ ትኩን ፡ መልእክቱ ፡ ዘታሠምሮ ፡ ለእግዚአብሔር ።

፩፻፷፫ ሥርዋጽ ፡ ተንግረ ፡ ውስተ ፡ ቀኖናተ ፡ ነገሥት ፡ ለብእሲት ፡ ትክት ፡ ወሐራስ ፡ ከመ ፡ ይጸልያ ፡ ጸሎተ ፡ በውስተ ፡ ቤት ፡ እኮ ፡ በውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።



ስሐ ፡ ጸሎት ፡ ነው ፡ ሙሴ ፡ አሮን ፡ ፊንሐስ ፡ ካህን ፡ እንደ፡መፀለያቸው ፡ ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ ይጸልዩ ፡ እንደ፡ነበር ።

፩፻፶፰ ከዚህም ፡ ቀጥሎ ፡ መጽሐፍ ፡ ያልከለከላት ፡ ፈቃድ ፡ የሚፈጸምባት ፡ ጸሎት ፡ ናት ፡ ልጅን ፡ እንደ፡መሻት ፡ ጥበብንም ፡ እንደ፡መሻት ፡ ሳሙኤልን ፡ እንደ ፡ አገኘች ፡ እንደ፡ሐና ፡ ጸሎት ፡ በወለደችውም ፡ ጊዜ ፡ እንደአመሰገነች ፡ (፩ኛ ፡ ሳሙ ፡ ፪ ፡ ፩-፲) ሐዋርያው ፡ "ጥበብን ፡ ያጣ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ሳይጠራጠር ፡ በሰፊው ፡ ወደሚሰጥ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይለምን ፡ እንዳለ" (ያዕ ፡ ፩ ፡ ፭) እርሱ ፡ ለለመነ ፡ ይሰጠዋል ። ጌታችንም ፡ በጸሎት ፡ የምትለምኑትን ፡ ሁሉ ፡ በሃይማኖት ፡ ትቀበላላችሁ ፡ ብሎ ፡ እንደ፡ተናገረ" (ማቴ ፡ ፳፩ ፡ ፳፪)

፩፻፶፱ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ልጆቻቸው ፡ የደ፡ገኙ ፡ አባቶች ፡ ጸሎት ፡ ነው ፡ እንደ ፡ ጳውሎስ ፡ ጸሎት ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ጢሞቴዎስንም ፡ በዚህ ፡ እንዳዘዘው ።

፩፻፷ ረስጠጅ ፡ ፵፫ ፡ ድስቅ ፡ ፴፫ ፡ ከተወገዘ ፡ ካህንና ፡ ከማያምን ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ መጸለይ ፡ አይገባም ፡ በቤትም ፡ ውስጥ ፡ ቢሆን ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ የጸለየ ፡ ይሻር ።

፩፻፷፩ ድስቅ ፡ ፰ ፡ ወንድሞቻችን ፡ ሆይ ፡ ዘወትር ፡ ትጸልዩ ፡ ዘንድ ፡ ይገባችኋል ። ያለአግባብ ፡ ዘወትር ፡ የሚቆሙ ፡ ሰዎች ፡ ቁጣን ፡ ወደ፡መተው ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ።

፩፻፷፪ ፲ ፡ የከበረ ፡ እንግዳ ፡ ባላገርም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሆይ ፡ ጸሎትህን ፡ አታቋርጥ ፡ ወንድሞች ፡ ከእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ይቀበሉት ፡ እንጂ ፡ ዲያቆኑም ፡ ቦታውን ፡ ያዘጋጅለት ፡ እንጂ ፡ አገልግሎቱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ የምታሰኘው ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ።

፩፻፷፫ ሥርዋጽ ፡ በነገሥታት ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ተነገረ ፡ ከግዳጅዋ ፡ ያልነፃች ፡ ሴትና ፡ አራስ ፡ ሴት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ሳይሆን ፡ በቤት ፡ እንዲጸልዩ ፡ በነገሥታት ፡ መጽሐፍ ፡ ተነገረ ።

## አንቀጽ ፡ ፲ወ፰ቱ ።

### በእንተ ፡ ኵሎሙ ፡ አጽዋም ።

፩፻፷፬ ጾምስ ፡ ተከልአተ ፡ ብእሲ ፡ እመብልዕ ፡ በጊዜ ፡ ዕዉቅ ፡ በውስተ ፡ ሕግ ፡ እንዘ ፡ ይትኤዘዝ ፡ ለዘ ሐነጾ ፡ ለሥርየተ ፡ አበሳ ፡ ወብዝኀ ፡ ዕሤት ፡ ፈቲዮ ፡ ኪያሁ ፡ ከመ ፡ ያድክም ፡ ኀይለ ፡ ፍት ወት ፡ ወትትአዘዝ ፡ ለነፍስ ፡ ነባቢት ።

፩፻፷፭ ወዘተእዘዘ ፡ ላዕለ ፡ ኵሎሙ ፡ ክርስቲያን ፡ ውእቱ ፡ ጾመ ፡ ፵ ፡ ዘጾመ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ዘይከውን ፡ ፍጻሜሁ ፡ በዓርበ ፡ ፍሥሕ ፡ እምዝኒ ፡ ሰሙነ ፡ ስቅለት ። ወእሉ ፡ ይጸወሙ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ መዓልት ፡ ወኢይት በላዕ ፡ በሙ ፡ እንስሳ ፡ ዘይወፅእ ፡ እምኔሁ ፡ ደም ፡ ወኢ ፡ ዘውእቱ ፡ እምእንስሳት ።

፩፻፷፮ ዓዲ ፡ ረቡዐ ፡ ወዓርበ ፡ በኵሉ ፡ ሰባዔ ፡ ዘእን በለ ፡ መዋዕለ ፡ ፶ ፡ ወበዓለ ፡ ልደት ፡ ወጥም ቀት ፡ ሶበ ፡ ኀብሩ ፡ በሙ ። ወይጼምዎሙ ፡ እስከ ፡ ፱ቱ ፡ ሰዓት ፡ በከመ ፡ ተጽሕፈ ።

፩፻፷፯ ወአጽዋምሰ ፡ ካልኣን ፡ እለ ፡ ተወሰኑ ፡ ላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ ወተሠርዑ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅብ ጣዊት ፡ ወእምኔሆሙ ፡ ዘይከውን ፡ በአምሳለ ፡ ጾም ፡ ዐቢይ ፡ በተጠናቅቆ ። ወይእቲ ፡ ሰሙነ ፡ ሕርቃል ፡ ዘትከውን ፡ እምቅድመ ፡ ጾም ፡ ዐቢይ ወጾመ ፡ ሰብአ ፡ ነነዌ ፡ ፫ቱ ፡ ዕለታት ። ወጾመ ፡ ድራረ ፡ ልደት ፡ ወጾመ ፡ ድራረ ፡ ጥምቀት ።

፩፻፷፰ ወእምኔሆሙ ፡ ዘየሐጽጽ ፡ እምእሉ ፡ ወይከ ውን ፡ ከመ ፡ ረቡዕ ፡ ወዓርብ ፡ ወውእቱ ፡ ጾም ፡ ዘይቀድም ፡ እምልደት ፡ ወጥንተ ፡ ዚአሁ ፡ መን ፈቀ ፡ ኅዳር ፡ ወፋሲካሁ ፡ በዓለ ፡ ልደት ።

፩፻፷፱ ወእምዝ ፡ ጾመ ፡ ሐዋርያት ፡ ወውእቱ ፡ ይትሉ ፡ እምበዓለ ፡ ሐምሳ ፡ ወፋሲካሁ ፡ እመ ፡ ፭ ፡ ለሐምሌ ፡ በዓለ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወጳውሎስ ።

፩፻፸ ወለእሉ ፡ አጽዋም ፡ ናሁ ፡ ጾምዎሙ ፡ ሕዝብ ፡ ምስለ ፡ ጕልቆ ፡ እምሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘይበ ዝኁ ፡ ጕልቆሙ ፡ እምጉባኤያት ፡ ኅዳጣን ፡ እለ ፡ ውኩፋት ፡ ቀኖናቲሆሙ ፡ ወይደሉ ፡ ዐቂ



## አንቀጽ ፡ ፲፰ ።

### ስለጾሞች ፡ ሁሉ ።

፩፻፷፬ ጾምስ ፡ በሕግ ፡ ውስጥ ፡ በታወቀው ፡ ጊዜ ፡ የሰው ፡ ከምግብ ፡ መከልከል ፡ ነው ፡ በደሉን ፡ ለማስተሥረይ ፡ ዋጋውን ፡ ለማብዛት ፡ እርሱን ፡ ወዶ ፡ ሕግን ፡ ለሠራለት ፡ እየታዘዘ ፡ የፈቲ ውን ፡ ኀይል ፡ ያደክም ፡ ዘንድ ፡ ለነባቢት ፡ ነፍስም ፡ ትታዘዝ ፡ ዘንድ ።

፩፻፷፭ ለክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ የታዘዘውም ፡ ጾም ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባውና ፡ ክርስቶስ ፡ የጾ መው ፡ ጾመ ፡ ፵ ፡ ነው ። ፍጻሜዋ ፡ ከፍሥሕ ፡ (የአይሁድ ፡ ፋሲካ) በፊት ፡ ባለው ፡ ዓርብ ፡ የሚሆን ፡ ነው ፡ ከዚህም ፡ ቀጥሎ ፡ የስቅለት ፡ ሳምንት ፡ ነው ። እነዚህም ፡ እስከ ፡ እሥራ ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ ይጾማሉ ፡ ደም ፡ የሚ ወጣው ፡ እንስሳ ፡ ከእንስሳትም ፡ የሚገኘው ፡ አይበላባቸውም ።

፩፻፷፮ ዳግመኛም ፡ በእየሳምንቱ ፡ ሁሉ ፡ ዓርብና ፡ ረቡ ዕን ፡ መጾም ፡ ነው ፡ በዓለ ፡ ፶ ፡ የልደትና ፡ የጥ ምቀት ፡ በዓል ፡ የተባበሩባቸው ፡ ጊዜ ፡ ካል ሆነ ፡ በቀር ፡ እንደተጻፈው ፡ እስከ ፱ ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ ይጾሟቸው ።

፩፻፷፯ በዚህ ፡ ላይ ፡ የተጨመሩ ፡ ሌሎች ፡ ጾሞች ፡ ግን በግብፅ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተጽፈዋል ። ከእነ ርሱም ፡ እንደ ፡ ዐቢይ ፡ ጾም ፡ በመጠንቀቅ ፡ የሚሆን ፡ አለ ፡ ይህችውም ፡ ከዐቢይ ፡ ጾም ፡ አስቀድማ ፡ የምትሆን ፡ የሕርቃል ፡ ጾም ፡ ናት ። የነነዌ ፡ ሰዎች ፡ ጾም ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ የልደትና ፡ የጥ ምቀት ፡ ዋዜማ ፡ ጾም ፡ (ገሀድ) ።

፩፻፷፰ ከእነርሱም ፡ የሚያንስ ፡ እንደ ፡ ረቡዕና ፡ እንደ ፡ ዓርብ ፡ የሚሆን ፡ አለ ፡ ይኸውም ፡ ከልደት ፡ አስቀድሞ ፡ የሚጾም ፡ ጾም ፡ ነው ፡ መጀመሪ ያው ፡ የኅዳር ፡ እኩሌታ ፡ ፋሲካው ፡ የልደት ፡ በዓል ፡ ነው ።

፩፻፷፱ ከዚህም ፡ ቀጥሎ ፡ ከበዓለ ፡ ፶ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለ ፡ የሐዋርያት ፡ ጾም ፡ ነው ፡ ፋሲካውም ፡ በጴጥ ሮስና ፡ በጳውሎስ ፡ በዓል ፡ ሐምሌ ፡ ፭ ፡ ቀን ፡ ነው ።

፩፻፸ እነዚህን ፡ ጾሞች ፡ ሕጎቻቸውን ፡ ከተቀበሏ ቸው ፡ በኋላ ፡ ከጥቂቶቹ ፡ ውሳኔዎች ፡ ቁጥራ ቸው ፡ ከሚበዛ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ወገን ፡ ከተቆ ጠሩት ፡ ጋር ፡ ሕዝቡ ፡ እነሆ ፡ ጾመዋቸዋል ።

ቦቶሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ሕጸጽ ።

፩፻፸፩ ወእምኔሆሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ዝንቱ ፡ በሀቤሆሙ ፡ ብዙኃን ፡ ሎቱ ፡ ወውእቱ ፡ ጾም ፡ በእንተ ፡ በዓለ ፡ እግዝእትነ ። ወፈድፋደሰ ፡ ዘይጸውምዎ ፡ ዕሙ ዳን ፡ ወመነኮሳት ፡ ወዮንቱ ፡ ቀዳሚ ፡ ነሐሴ ፡ ወበዓለ ፡ እግዝእትነ ፡ ፋሲካሁ ።

፩፻፸፪ ወበእሉ ፡ አጽዋም ፡ እለ ፡ ተሠርዑ ፡ ይጹሙ ፡ እስከ ፡ ፱ቱ ፡ ሰዓት ፡ እምዕለት ፡ ወኢይብልዑ ፡ በሙ ፡ ሥጋ ፡ ዘእንበለ ፡ ዓሣ ፡ ወዘሰ ፡ አፈድፈደ ፡ ጾመ ፡ እምዝንቱ ፡ ዘተሠርዐ ፡ ይፈደፍድ ፡ ዕሤቱ ። ወኢይጹሙ ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ ወበሰንበት ፡ ዘእንበለ ፡ ጥሉላት ።

፩፻፸፫ ወጾምሰ ፡ ጸባሒተ ፡ ሥጋ ፡ ውእቱ ፡ በከመ ፡ ምጽዋት ፡ ጸባሒተ ፡ ንዋይ ፡ ይእቲ ። ወመፍቅደ ፡ ሕግሰ ፡ በጾም ፡ ከመ ፡ ትድክም ፡ ኀይለ ፡ ፍትወት ፡ ወትትእዘዝ ፡ ለነፍስ ፡ ነባቢት ፡ በከመ ፡ መፍቅዳ ፡ ለጸሎት ፡ በዘትትኤዘዝ ፡ ኀይለ ፡ መዓት ፡ ለልብ ።

፩፻፸፬ ወእምረባኅቱ ፡ ጾም ፡ ንትሜሰል ፡ በመንፈሳውያን ፡ ወበተመስሎት ፡ ይትከሀል ፡ ከመ ፡ ይብጻሕ ፡ ተመሳሊሆ ፡ ኀበ ፡ ተመስሎ ። ወካዕበ ፡ ከመ ፡ ያእምር ፡ ጸዋሚ ፡ ሕማመ ፡ ረኃብ ፡ ወይምሕሮሙ ፡ ለርኁባን ፡ ወለእለ ፡ ይስእሉ ። ወካዕበ ፡ ከመ ፡ ይትመጠው ፡ ቍርባነ ፡ እንዘ ፡ ውእቱ ፡ በጽኑዕ ፡ ፍትወት ፡ ለተሲስዮቱ ። ወይኩን ፡ ተመጥዎቱ ፡ በጸሒቅ ፡ ነፍሳዊ ፡ ወሥጋዊ ። ወዓዲ ፡ ከመ ፡ ያምልኮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በተለንቶቱ ፡ በአሥንዮተ ፡ ጾም ፡ እመንገለ ፡ ተአንስሶ ፡ ወበጸሎት ፡ እመንገለ ፡ ነባብያን ፡ ወበቀዋሚት ፡ ንቡራት ፡ በእንተ ፡ አጽዋም ።

፩፻፸፭ ድስቅ ፡ ፳ወ፱ቱ ፡ ወይኩኑን ፡ በንቢያሆሙ ፡ ከቡረ ፡ ጾመ ፡ ፵ ፡ ወዮንቱኒ ፡ በዕለተ ፡ ሰኑይ ፡ ዳግማዊ ፡ እምሰንበታት ፡ ወፍጻሜሁ ፡ በዕለተ ፡ ዓርብ ፡ እምቅድመ ፡ ፋሲካ ። ይኤምር ፡ ኀበ ፡ ሰባዒ ፡ እንተ ፡ እምድኅሬሃ ፡ ሰባዒ ፡ ፋሲካ ። ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ጾሙ ፡ ከመ ፡ ትፈጽሙ ፡ ሰሙነ ፡ ፋሲካ ፡ ትጹሱ ፡ እምድኅረ ፡ ጾም ።

፩፻፸፮ ሥርዖጽ ፡ ይትበወት ፡ ሰሙነ ፡ ፋሲካ ፡ እንተ ፡ እምድኅሬሃ ፡ ሰሙነ ፡ ፋሲካ ፡ ወከማሁ ፡ እዘ



ያስሕበዕም ፡ ሊጠብቋቸው ፡ ይገባል ።

፩፻፸፩ ከእነዚህም ፡ ሌላ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ጠብቀው ፡ የሚጾሙት ፡ አለ ፡ ይኸውም ፡ ጾም ፡ ስለእመቤታችን ፡ በዓል ፡ ነው ። ይልቁንም ፡ መናኒዎች ፡ መነኰሳቱ ፡ የሚጾሙት ፡ መጀመሪያው ፡ ነሐሴ ፩ ፡ ቀን ፡ ፋሲካው ፡ የእመቤታችን ፡ በዓል ፡ ነው ።

፩፻፸፪ በእነዚህ ፡ በታዘዙት ፡ ጾሞች ፡ ከቀኑ ፡ እስከ ፡ ፱ ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ ይጹሙ ፡ ከዓሣ ፡ በቀር ፡ ሥጋ ፡ አይብሉባቸው ። ከዚህ ፡ ከታዘዘው ፡ አብልጦ ፡ የጾመ ፡ ግን ፡ ዋጋው ፡ ይበዛለታል ፡ ከጥሉላት ፡ በቀር ፡ እሑድ ና ፡ ቅዳሜ ፡ አይጹሙ ።

፩፻፸፫ ጾምስ ፡ የሥጋ ፡ ግብር ፡ ነው ፡ ምጽዋት ፡ የገንዘብ ፡ ግብር ፡ እንደሆነ ። ሕግ ፡ ጾምን ፡ ያስወደደው ፡ የፈቲው ፡ ኃይል ፡ ትደክም ፡ ዘንድ ፡ ለነባቢት ፡ ነፍስም ፡ ትታዘዝ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ጸሎትን ፡ ያሻው ፡ ፈቃድ ፡ ለልብ ፡ የቁጣ ፡ ኀይል ፡ እንድትታዘዝ ፡ እንደ ፡ ሆነ ።

፩፻፸፬ ጾም ፡ ይረባናል ፡ ብለን ፡ ከመጾማችን ፡ የተነሣ ፡ መንፈሳውያንን ፡ እንመስላለን ፡ ከመስላናቸውም ፡ የሚመስሉትን ፡ ለመምሰል ፡ ይቻላል ። ዳግመኛም ፡ ጿሚው ፡ የረኃብን ፡ ችግር ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ ለተራቡትና ፡ ለሚለምኑት ፡ ይራራላቸው ። ዳግመኛም ፡ በፅኑዕ ፡ ፈቃድ ፡ ሁኖ ፡ ሊመገበው ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ መቀበሉም ፡ በሥጋዊና ፡ በነፍሳዊ ፡ ትጋት ፡ ይሁን ፡ ዳግመኛም ፡ ከእንስሳዊ ፡ ባሕርይ ፡ ተለይቶ ፡ የጾምን ፡ ሥርዓት ፡ ጠብቆ ፡ ከሰው ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ በጸሎት ፡ የተለየ ፡ ሁኖ ፡ ስለ ፡ አጽዋም ፡ በተሠሩት ፡ ሕጎች ፡ የፀና ፡ ሁኖ ፡ በሁለንተናው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያምልከው ።

፩፻፸፭ ድሰቅ ፡ ፳፱ ፡ ጾመ ፡ ፵ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ የከበረ ፡ ይሁን ፡ መጀመሪያውም ፡ ከሰንበቶቹ ፡ ሁለተኛ ፡ የሆነው ፡ ሰኞ ፡ ነው ፡ መጨረሻውም ፡ ከፋሲካ ፡ አስቀድሞ ፡ ባለው ፡ በዕለተ ፡ ዓርብ ፡ ነው ። ይህም ፡ ከፋሲካ ፡ ሱባዔ ፡ በኋላ ፡ ያለ ፡ ሱባዔ ፡ እንደሆነ ፡ ያስረዳል ፡ ከዚህ ፡ ጾም ፡ በኋላ ፡ የከበረ ፡ ሰሙነ ፡ ሕማማትን ፡ ትፈጽሙ ፡ ዘንድ ፡ ትጉ ።

፩፻፸፮ ሥርዓቱ ፡ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የፋሲካ ፡ ሳምንት ፡ የሚሆን ፡ ሰሙነ ፡ ፋሲካ ፡ (የአይሁድ ፡ ፋሲካ)

ዙኑ ፡ ከመ ፡ ንጹም ፡ እሎንተ ፡ ሰዱሰ ፡ መዋ
ዕለ ፡ ወከመ ፡ ንጹም ፡ ረቡዐ ፡ ወዓርበ ፡ ለለሱ
ባዔ ። እስመ ፡ ዝንቱ ፡ በእንተ ፡ ፈጸሞቱ ፡
ምክር ፡ ቦቱ ፡ ወዘኒ ፡ በእንተ ፡ ፈጸሞቱ ፡
ፈቃዱ ፡ ለመድኀኒነ ። ወያሰርፉ ፡ እምጾም ፡
በዕለት ፡ ሳብዒት ፡ ጊዜ ፡ ንቅወተ ፡ ዶርሆ ።

፳፻፷፯ ወኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይጹሙ ፡ በዕለተ ፡ ሰንበት ፡
ወትረ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አዕረፈ ፡ ቦቱ ፡
እምኵሉ ፡ ግብሩ ፡ አላ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይጹሙ ፡
በዝንቱ ፡ ሰንበት ፡ ባሕቲቱ ፡ እስመ ፡ ፈጣሬ ፡
ፍጥረታት ፡ ኮነ ፡ ቦቱ ፡ ስኩበ ፡ ውስተ ፡ መቃ
ብር ።

፳፻፷፰ ዘ፬ ፡ ወበእሉ ፡ ፮ቱ ፡ ዕለታት ፡ ኢይብልዑ ፡
በሙ ፡ እንበለ ፡ ኅብስት ፡ ወጼው፡ ወማይ ፡
ባሕቲቱ ፡ ወእምወይንሰ ፡ ወሥጋ ፡ ተግኅሡ ፡
በእሉ ፡ ዕለታት ። እስመ ፡ ዕለታተ ፡ ኀዘን ፡
እሙንቱ ፡ ወኢኮኑ ዕለታተ ፡ በዓላት ፡ ለሰ
ለተ ፡ ዓርብሰ ፡ ወሰንበት ፡ ጹምዎሙ ፡ ለ፪
ሆሙ ፡ ኅቡረ ፡ ወዘይክል ፡ ኢይጥዓም ፡ምን
ተኒ ፡ ቦቱን ፡ እስከ ፡ ጊዜ ፡ ንቅወተ ፡ ዶርሆ ፡
ዘሌሊት ፡ ወለእመሰ ፡ ኢክህለ ፡ ብእሲ ፡ ከመ ፡
ይጹም ፡ ፪ሆን ፡ ዕለታተ ፡ ኅቡረ ፡ ይዕቀብ ፡
ጾመ ፡ ዕለተ ፡ ሰንበት ።

፳፻፷፱ ይቤ ፡ እግዚእ ፡ በእንተ ፡ ነፍሱ ፡ አመ ፡ ነሥ
እዎ ፡ ለመርዓዊ ፡ እምኔሆሙ ፡ አሜሃ ፡ ይጾ
ሙሙ ። ወአንትሙኒ ፡ ጹሙ ፡ በእሉ ፡ ዕለታት ፡
እስከ ፡ ሌሊት ፡ በከመ ፡ ገበርነ ፡ ንሕነ ፡ አመ ፡
ነሥእዎ ፡ እምኔነ ።

፳፻፸ ወእምድኅረ ፡ ፈጸምክሙ ፡ ገቢረ ፡ በዓለ ፡ ፃ ፡
ግበሩ ፡ ካዕበ ፡ በዓለ ፡ ሰቡዐ ፡ መዋዕለ ፡ ካልእ ፡
ወእምዝ ፡ ጹሙ ፡ እምድኅረ ፡ አዕረፍክሙ ።
ወዓዲ ፡ ንኤዝዘክሙ ፡ ከመ ፡ ትጹሙ ፡ ወትረ ፡
ረቡዐ ፡ ወዓርበ ፡ ወእመሰ ፡ ይትከሀለክሙ ፡
ፈድፋደ ፡ እምዝንቱ ፡ ጹሙ ፡ ወሀቡ ፡ ምጽዋተ፡
ኀነዳያን ።

፳፻፸፩ ሥርዋጽ ፡ እምቃለ ፡ መምህር ፡ ኅሩይ ፡ አባ
ዲዩ ፡ ለዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ ይምሐር ፡ እግዚአ
ብሔር ። ወትእምርቱሰ ፡ ለዝንቱ ፡ ሰባዔ ፡
ከመ ፡ ኢመፍትው ፡ ለነ ፡ ንብላዕ ፡ ቦቱ ፡ ናሁ ፡
መካን ዘአዘዘነ ፡ ቦቱ ፡ በጾዊመ ፡ ረቡዕ ፡ ወዓ



እንደሆን ፡ ይታወቃል ፡ እንደዚሁም ፡ እነዚህን ፡
ስድስቱን ፡ ቀኖች ፡ እንጾም ፡ ዘንድ ፡ አዘዙን ፡
በየሳምንቱም ፡ ረቡዕንና ፡ ዓርብን ፡ እንጾም ፡
ዘንድ ፡ አዘዙን ። ይኸውም ፡ ምክር ፡ የተፈጸ
መበት ፡ ነውና ፡ ይኸኛውም ፡ መድኀኒታችን ፡
ፈቃዱን ፡ ስለፈጸመበት ፡ ነውና ፡ በሰባተኛው ፡
ቀን ፡ ዶሮ ፡ በሚጮኽ ፡ ጊዜ ፡ ከጾም ፡ ይረፉ ።

፳፻፷፯ ዘወትር ፡ ዘዕለተ ፡ ሰንበት ፡ መጾም ፡ አይገ
ባም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሥራው ፡ ሁሉ ፡ አርፎ
በታልና ፡ ቅዳሜ ፡ ስዑርን ፡ ብቻ ፡ ሊጾሙ ፡ ይገ
ባል ፡ እንጂ ። የፍጥረታቱ ፡ ሁሉ ፡ ፈጣሪ ፡ በመ
ቃብር ፡ ውስጥ ፡ አድሮበታልና ።

፳፻፷፰ ፬ ፡ በሊህ ፡ በስድስቱ ፡ ቀኖች ፡ ከቂጣ ፡ ከጨው
ከውኃ ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ አይብሉባቸው ፡ በሊህ ፡
ቀኖች ፡ ከወይን ፡ ከሥጋ ፡ ተለዩ ፡ የኀዘን ፡ ቀኖ
ች ፡ ናቸውና ፡ የደስታ ፡ ቀኖች ፡ አይደሉም ፡
ዓርብንና ፡ ቅዳሜን ፡ ግን ፡ ሁለቱንም ፡ በአንድ
ነት ፡ ጹሟቸው ። የሚችል ፡ እስከ ፡ ሌሊቱ ፡
ዶሮ ፡ ጩኸት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ምንም ፡ ምን ፡
አይቅመስባቸው ፡ ሰውየው ፡ ሁለቱን ፡ ቀኖች ፡
በአንድነት ፡ መጾም ፡ባይቻለው ፡ ግን ፡ የቅዳ
ሜን ፡ ጾም ፡ ይጹም ።

፳፻፷፱ ጌታ ፡ ስለ ራሱ ፡ እንዲህ ፡ አለ ። "ሙሽራ
ውን ፡ ከእነርሱ ፡ለይተው ፡ በወሰዱት ፡ ጊዜ ፡
ያንጊዜ ፡ ይጾማሉ" (ማቴ ፡ ፱ ፡ ፲፭) እናንተም ፡
በእነዚህ ፡ ቀኖች ፡ እስከ ፡ ሌሊት ፡ ድረስ ፡
ጹሙ ፡ ሙሽራውን ፡ ከእኛ ፡ ለይተው ፡ በወሰ
ዱት ፡ ጊዜ ፡ እኛ ፡ እንደ ፡ ጾምን ።

፳፻፸ በዓለ ፡ ፃን ፡ ከጨረሳችሁ ፡ በኋላ ፡ ዳግመኛ ፡
ሰባት ፡ ቀን ፡ ሌላ ፡ በዓል ፡ አድርጉ ፡ ከዚህም ፡
ቀጥሎ ፡ ከአረፋችሁ ፡ በኋላ ፡ ጹሙ ። ዳግመኛ
ም ፡ ረቡዕንና ፡ ዓርብን ፡ ዘወትር ፡ ትጾሙ ፡
ዘንድ ፡ እናዝዛችኋለን ፡ የሚቻላችሁስ ፡ ከሆነ ፡
ከዚህ አብልጣችሁ ፡ ጹሙ ፡ ለድሆችም ፡ ምጽ
ዋት ፡ ስጡ ።

፳፻፸፩ ሥርዋጽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቅር ፡ ይበለውና ፡
ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ከሰበሰበው ፡ የተመረጠ ፡
ከሆነው ፡ መምህር ፡ ቃል ፡ የተገኘ ፡ ነው ፡ የዚህ
ሳምንት ፡ ምልክት ፡ ግን ፡ ልንበላበት ፡ እንደማ
ይገባ ፡ እነሆ ፡ ረቡዕንና ፡ ዓርብን ፡ እንድንጾም ፡
ያዘዘበት ፡ አንቀጽ ፡ አለ ፡ ዳግመኛም ፡ በዓለ ፡

ርብ ፡ ወደገመ ፡ ቦቱ ፡ ዘክሮቀ ፡ ፶ ፡ ወልደት ፡ ወጥምቀት ፡ ወኢደገመ ፡ ዘክሮቀ ፡ ዝንቱ ፡ ሱባዔ ፡ ሶበሰ ፡ ኮነ ፡ እመዋዕል ፡ እለ ፡ ይበልዑ ፡ ውስቴታ ፡ ወዘኢይደሉ ፡ ጾሞ ፡ በውስቴቱ ፡ ከመ ፡ እልከቱ ፡ እምደገመ ፡ ዘክሮቶ ።

፭፻፹፪ ወካዕበ ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ መዋዕላት ፡ እለ ፡ አዘዙነ ፡ ከመ ፡ ኢንጹም ፡ ወኢንስግድ ፡ ቦቶን ፡ ከመ ፡ እሑድ ፡ ወሰንበት ፡ ወበዓላተ ፡ እግዚእ ፡ ኢዘከረ ፡ ምስሌሆን ፡ ዘንተ ፡ ሱባዔ ። ወካዕበ ፡ ለዘንበሮ ፡ ገቢረ ፡ ግብረ ፡ ሕማማት ፡ ተአዘዘ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ህየንቴሃ ፡ እምድኅረ ፡ በዓለ ፡ ፶። ወለእመሰ ፡ ኮነ ፡ ዝንቱ ፡ ሱባዔ ፡ ዘእምድኅረ ፡ በዓለ ፡ ፶ ፡ ዘይደሉ ፡ ከመ ፡ ይብልዑ ፡ ቦቱ ፡ እምድኅረ ፡ ፶ ፡ ዕለታት ፡ እምተብህለ ፡ ወእምድኅሬሁ ፡ ካዕበ ፡ ወዓዲ ፡ ካዕበ ። ወዘተብህለሰ ፡ አብዕሉ ፡ ቦቱ ፡ እስመ ፡ ኢይቤ ፡ በእንቲአሁ ፡ ዘእንበለ ፡ ግበሩ ፡ በዓለ ።

፭፻፹፫ ሥርዋጽ ፡ ዝንቱሰ ፡ ይኤምር ፡ ኀበ ፡ ጾመ ፡ ረቡዕ ፡ ወዓርብ ፡ ውስቴቱ ፡ ወኢይኤምር ፡ ከመ ፡ ይፈጽሙ ፡ ኪያሆሙ ። ወናሁ ፡ ይቤሉ ፡ ባስልዮስ ፡ ወአፈወርቅ ፡ እስመ ፡ ገቢረ ፡ በዓልሰ ፡ አኮ ፡ መብልዕ ፡ ውእቱ ፡ ወዓዲ ፡ ዕውቅ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ገቢረ ፡ በዓል ፡ በጾም ፡ ውእቱኬ ከመ ፡ ይትነበብ ፡ ዘይደሉ ፡ ለበዓል ፡ ወአኮ ፡ ከመ ፡ ይብልዑ ፡ ቦቱ ። ወናሁ ፡ አዘዙነ ፡ ቀኖና ከመ ፡ ናብዕል ፡ ፫ተ ፡ ዕለታተ ፡ ሶበ ፡ ተሠይመ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወእሙር ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ንሕነ ፡ ኢንበልዕ ፡ በእላ ፡ ሠላስ ፡ መዋዕላት ፡ ለእመ ፡ ኮኑ ፡ በጾም ፡ ወገቢረ ፡ በዓል ፡ አኮ ፡ ውእቱ ፡ በበሊዕ ።

፭፻፹፬ ወዓዲ ፡ ናሁ ፡ ኀተሙ ፡ ዘንተ ፡ ቀኖና ፡ በብሂሎቶሙ ፡ እመ ፡ ይትከሀለክሙ ፡ ፈድፋደ ፡ እምዝንቱ ፡ ጹሙ ፡ ወለእመሰ ፡ መጽአ ፡ በእንቲአሁ ፡ ተጋእዞ ፡ ጸዊሞቱ ፡ ድልው ፡ ወይኄይስ ፡ ፈድፋደ ፡ እመብልዕ ።

፭፻፹፭ ወካዕበ ፡ እስመ ፡ በ ፡ እምጉባኤያት ፡ ዘይከውን ፡ ኍልቆሙ ፡ መጠነ ፡ ፳ ፡ ጉባኤ ፡ ወነዋ ፡ ጾምነ ፡ ዘንተ ፡ ጾመ ፡ በውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ሱባኤ ፡ እስከ ፡ መዋዕለ ፡ እለ ፡ ፈድፈደ ፡ ኍልቆሙ ፡ እምዝንቱ ፡ ኍልቍ ፡ እምሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእለ ፡ እስክንድርያ ። ወለእመ ፡ ተዐዶነ ፡ ትእ



፶ ፡ ልደት ፡ ጥምቀት ፡ ቢውልባቸው ፡ አትጹሙ ብሎ ፡ ያዘዘበት ፡ አንቀጽ ፡ አለ ። ስለዚህ ፡ ሳምንት ፡ ግን ፡ አልተናገረም ። ቢበሉባቸው ፡ በሚገባ ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፡ ሊጾሙባቸው ፡ የማይገባ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ እንደእነዚያ ፡ መልሶ ፡ በተናገረ ፡ ነበር ።

፭፻፹፪ ዳግመኛም ፡ እንዳንጾምባቸው ፡ እንዳንበግድባቸው ፡ የታዘዝንባቸው ፡ ቀኖች ፡ እንደ ፡ እሑድ፡ እንደ ፡ ሰንበት ፡ እንደ ፡ ጌታ ፡ በዓላት ፡ ያሉ ፡ ቀኖች ፡ አሉና ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ይህን ፡ ሳምንት አልተናገረም ። ዳግመኛም ፡ የሰሙነ ፡ ሕማማትን ፡ ሥራ ፡ ሳይሠራ ፡ ላለፈበት ፡ ከበዓለ ፡ ፶ ፡ በኋላ ፡ ለለርሰዋ ፡ መጾም ፡ መስገድ ፡ ይገባ ፡ ዘንድ ፡ ታዘዘ ። ከበዓለ ፡ ፶ ፡ በኋላ ፡ የሚውለው ፡ ሳምንት ፡ ይህ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ከ፶ ፡ ቀኖች ፡ በኋላ ፡ ይበሉበት ፡ ዘንድ ፡ የሚገባ ፡ ቢሆን፡ እንደገና ፡ ብሉበት ፡ በተባለ ፡ ነበር ። በዓል ፡ አድርጉ ፡ ማለቱ ፡ ግን ፡ በዓል ፡ አድርጉ ፡ ከማለቱ ፡ በቀር ፡ ብሉበት ፡ አላለምና ።

፭፻፹፫ ሥርዋጽ ፡ ይህስ ፡ በውስጡ ፡ ያሉትን ፡ የዓርብንና ፡ የረቡዕን ፡ ጾም ፡ ያበረዳል ። እነርሱንም ፡ ይፈጽሟቸው ፡ ዘንድ ፡ አያስረዳም ፡ እነሆ ፡ ባስልዮስና ፡ አፈወርቅ ፡ እንዲህ ፡ አሉ ፡ በዓል ፡ ማክበር ፡ በመብል ፡ አይደለምና ፡ ዳግመኛም ፡ በጾም ፡ በዓል ፡ ማክበር ፡ እንዲገባ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ለበዓሉ ፡ የሚስማማው ፡ እንዲነበብ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሊበሉበት ፡ አይደለም ። ኤጲስቆጶስ ፡ በተሾመ ፡ ጊዜ ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ እንድናከብር ፡ እነሆ ፡ ቀኖና ፡ አዘዘችን ። በጾም ፡ ቀን ፡ እንኳ ፡ ቢሆን ፡ በእነዚህ ፡ በ፫ ፡ ቀኖች ፡ እንዳንበላ ፡ የታወቀ ፡ ነው ፡ በዓል ፡ ማክበር ፡ በመብል ፡ አይደለም ።

፭፻፹፬ ዳግመኛም ፡ ቢቻላችሁ ፡ ከዚህ ፡ አብዝታችሁ ፡ ጹሙ ፡ በማለታቸው ፡ ይህን ፡ ሕግ ፡ እነሆ ፡ ወሰኑ ፡ በጾሙ ፡ ምክንያት ፡ ጠብ ፡ ክርክር ፡ ቢሆን ፡ መጾም ፡ ይገባል ። ከመብላት ፡ በጣም ፡ ይሻላል ።

፭፻፹፭ ዳግመኛም ፡ ከተሰበሰቡት ፡ ወገን ፡ ቍጥራቸው ኻያ ፡ የሚሆኑት ፡ ጉባኤዎች ፡ ጹመውታልና ፡ ከእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ወገን ፡ ከዚህ ፡ ቍጥር ፡ ቍጥራቸው ፡ እስከ ፡ በዙት ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ድረስ ፡ በዚህ ፡ ሳምንት ፡ እነሆ ፡ ይህን ፡ ጾም ፡ ጾምነ ። የማኅበሩን ፡ ትእዛዝ ፡ ብንተላለፍ ፡

ዛዛተ ፡ ማኅበር ፡ ዝንቱስ ፡ ኢኮነ ፡ ሠናየ ፡ ወረሰይነ ፡ ዘንተ ፡ ማኅበረ ፡ ሕሡመ ፡ ፈድፋደስ ፡ ሶበ ፡ ተቃወመ ፡ ትሩፋተ ፡ ሕገጋቲነ ፡ ዘውእቱ ፡ እክይ ፡ በእዑቆተ ፡ ስሰዕት ፡ በእንተ ፡ መባልዕት ።

፩፻፺፮ ወካዕበ ፡ በከመ ፡ ጾመ ፡ ሙሴ ፡ እምቅድመ ፡ ይንግሮሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ሕገ ፡ ኦሪት ፡ ዘነሥአ ፡ እግዚአብሔር ፡ በበዓለ ፡ ፶ ። ወእግዚእነሂ ፡ ጾመ ፡ እምድኅረ ፡ ርደተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ላዕሌሁ ፡ እምቅድመ ፡ ይንግሮሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ሕገ ፡ ዚአሁ ። ወከማሁ ፡ ጾሙ ፡ ሐዋርያትኒ ፡ ሶበ ፡ ወረደ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በበዓለ ፡ ፶ ፡ ቅድመ ፡ ተናብቦቶሙ ፡ ለሕዝብ ፡ በሕግ ፡ መሢሐዊት ፡ ወንሕነኒ ፡ ተመራሕነ ፡ ቦሙ ፡ በዝንቱ ። ወበዝየ ፡ ኮነ ፡ ፍጻሜ ፡ ሥርዋጽ ።

፩፻፺፯ ረስጣ ፡ ፳ወ፰ቱ ፡ ወሶበ ፡ ተሰነአወ ፡ ውኀብረ ፡ ዕለተ ፡ ልደት ፡ በዕለታተ ፡ ጾም ፡ ዘውእቶሙ ፡ ረቡዕ ፡ ወዓርብ ፡ ይጸልዩ ፡ ወይትመጠዉ ፡ እምሥጢራተ ፡ ቅድሳት ፡ ወኢይፍትሑ ፡ ጾመ ፡ እስከ ፡ ፱ቱ ፡ ሰዓት ።

፩፻፺፰ ረስጠብ ፡ ፵ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ፩ዱ ፡ ውስተ ፡ ቀላይ ፡ ወኢያእመረ ፡ ዕለተ ፡ ሕማማት ፡ ይጹም ፡ እምድኅረ ፡ በዓለ ፡ ፶ ፡ እኮ ፡ ውእቱ ፡ ዕለተ ፡ ሕማማት ፡ ዘየዐቅብ ፡ እላ ፡ እምሳሊሁ ፡ ውእቱ፡ ባሕቱ ፡ ይደሉ ፡ ላሰሌሁ ፡ ጾም ፡ ህየንቴሁ ።

፩፻፺፱ ረስጠጅ ፡ ፰ ፡ ረስጠብ ፡ ፵ወ፰ቱ ፡ ወዘኢይጸውም ፡ ጾመ ፡ ፵ ፡ ወረቡዕ ፡ ወዓርብ ፡ እመ ፡ ኮነ ፡ ካህነ ፡ ይትመተር ፡ ዘእንበለ ፡ ዘሀሎ ፡ ዘቦቱ ፡ ደዌ ፡ ክሡት ፡ ወእመኒ ፡ ኮነ ፡ ሕዝባዌ ፡ ይትፈለጥ ።

፩፻፪ ረስጠብ ፡ ፵ ፡ ረስጠጅ ፡ ፺ቱ ፡ ወእመ ፡ ገብረ ፡ ካህን ፡ ግብረ ፡ ሕማማት ፡ እምቅድመ ፡ ያዕረ ፡ ሌሊተ ፡ ወመዓልተ ፡ ይትፈለጥ ። ወእመቦ ፡ ዘተረከበ ፡ እምካህናት ፡ እንዘ ፡ ይጸውም ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ አው ፡ በዕለተ ፡ ሰንበት ፡ ዘእንበለ ፡ ሰንበት ፡ ዐባይ ፡ ባሕቲታ ፡ ዘድኅረ ፡ ሕማማት ፡ ይትመተር ።

፩፻፪፩ ዶቅ ፡ ፴ወ፩ዱ ፡ ወኢይደሉ ፡ በጾመ ፡ ፵ ፡ ከመ ፡ ናብዕል ፡ ዕለተ ፡ ሰማዕታት ፡ እላ ፡ ይኩን ፡ ተዝካረ ፡ ሰማዕታት ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ ወሰንበት ።

፩፻፪፪ ዘ፶ወ፱ቱ ፡ ወኢይደሉ ፡ በጾመ ፡ ፵ ፡ ገቢረ ፡ ከብ

ይህን ፡ ማኅበር ፡ እንዲነቀፍ ፡ ብናደርግ ፡ ደግ ፡ አይደለም ። ይልቁንም ፡ የሕጋችንን ፡ ትሩፋት ፡ በተቃወመ ፡ ጊዜ ። ይኸውም ፡ ስለመብል ፡ ስስትን ፡ በመግለጽ ፡ የሚደረግ ፡ ክፋት ፡ ነው ።

፩፻፺፮ ዳግመኛም ፡ ስለ ፡ ሃኛው ፡ ቀን ፡ አከባበር ፡ ሙሴ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የተቀበለውን ፡ ሕገ ፡ ኦሪት ፡ ለሕዝቡ ፡ ከማስተማሩ ፡ በፊት ፡ እንደጾመ ፡ (ዘፀ ፡ ፴፬ ፡ ፳፰) ጌታችንም ፡ በርሱ፡ ላይ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከወረደ ፡ በኋላ ፡ የርሱን ፡ ሕግ ፡ ለሕዝብ ፡ ከማስተማሩ ፡ አስቀድሞ ጾመ ። ሐዋርያትም ፡ በበዓለ ፡ ፶ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በወረደላቸው ፡ ጊዜ ፡ ሕገ ፡ ወንጌልን ፡ ለሕዝቡ ፡ ከማስተማራቸው ፡ አስቀድሞ ፡ እንደዚሁ ፡ ጾሙ ። እኛም ፡ በዚህ ፡ በእነርሱ ፡ ተመራን ፡ የሥርዋጽ ፡ ፍጻሜ ፡ በዚህ ፡ ሆነ ።

፩፻፺፯ ረስጣ ፡ ፳፰ ፡ ልደት ፡ በጾም ፡ ቀኖች ፡ ረቡዕና ፡ ዓርብ ፡ ቢውል ፡ ይጸልዩ ። ሥጋውንና ፡ ደሙንም ፡ ይቀበሉ ፡ እስከ ፡ ዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ ጾሙ ፡ ብሰው ፡ አይፍረዱ ።

፩፻፺፰ ረስጠብ ፡ ፵ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በባሕር ፡ ቢኖር ፡ ሰሙነ ፡ ሕማማትን ፡ ባያውቅ ፡ ከበዓለ ፡ ፶ ፡ በኋላ ፡ ይጹም ። ይኸውም ፡ ሰሙነ ፡ ሕማማትን ፡ የሚጠብቅ ፡ አይደለም ። ምሳሌውን ፡ ብቻ ነው ፡ እንጂ ፡ ስለእርሱ ፡ መጾም ፡ ይገባዋል ።

፩፻፺፱ ረስጠጅ ፡ ፰ ፡ ረስጠብ ፡ ፵፰ ፡ ሀቢይ ፡ ጾምንና ፡ ዓርብን ፡ ረቡዕን ፡ የማይጾም ፡ የታወቀ ፡ ደዌ ፡ ያለበት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ካህን ፡ ቢሆን ፡ ይሻር ፡ ሕዝባዊ ፡ ቢሆንም ፡ ይለይ ።

፩፻፪ ረስጠብ ፡ ፵ ፡ ረስጠጅ ፡ ፺ ፡ ካህን ፡ ሰሙነ ፡ ሕማማትን ፡ ቀንና ፡ ሌሊቱን ፡ ሳያስተካክል ፡ አስቀድሞ ፡ ቢያውል ፡ ይሻር ። ከሕመማት ፡ ቀጥሎ ፡ ከምትሆን ፡ ከቅዳሜ ፡ ስዑር ፡ በቀር ፡ እሑድንና ፡ ቅዳሜን ፡ የጾመ ፡ ካህን ፡ ቢኖር ፡ ይሻር ።

፩፻፪፩ ዶቅ ፡ ፴፩ ፡ በዐቢይ ፡ ጾም ፡ የሰማዕታትን ፡ በዓል ፡ ልናከብር ፡ አይገባንም ። የሰማዕታት ፡ መታሰቢያ ፡ በእሑድ ፡ በቅዳሜ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ።

፩፻፪፪ ፶፱ ፡ በ፵ ፡ ጾም ፡ ሠርግ ፡ ማድረግ ፡ አይገ

ካብ ፡ ወኢ.ብእሲት ፡ ሶበ ፡ ትወልድ ፡ ወኢ.ይጸ ውዑ ፡ ሰብእ ፡ ኀበ ፡ መካን ፡ ስቴ ፡ ለሰትዩ ።

፩፻፺፫ በስ ፡ ሯወ፫ቱ ፡ ወኢ.ይደሉ ፡ ይስተዩ ፡ መኑሂ ፡ እምካህናት ፡ ወይነ ፡ በጾመ ፡ ፵ ፡ ወኢ.በጾመ ፡ ረቡዕ ፡ ወዓርብ ፡ ወኢ.ይባእ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ምሕፃብ ፡ ወኢ.ይኑም ፡ ብእሲ ፡ ምስለ ፡ ብእ ሲቱ ፡ በመዋዕለ ፡ ጾም ፡ ዘ፵ ።

፩፻፺፬ ወሶበ ፡ ኀብረ ፡ በዓለ ፡ ሰማዕታት ፡ ምስለ ፡ ጾም ፡ እመ ፡ አብዐለ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አው ፡ ቀሲስ ፡ በመብልዕ ፡ ለሕዝብ ፡ በእንተ ፡ ምክ ንያተ ፡ ሞቶሙ ፡ ለሰማዕታት ፡ ይትመተር ፤ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ኮነ ፡ ምክንያተ ፡ እከይ ፡ ላዕለ ፡ ነፍሳት ፡ ብዙኃት ። ወእመሰ ፡ በልዑ ፡ እሙ ንቱ ፡ በፈቃዶሙ ፡ ይስድዶሙ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አው ፡ ቀሲስ ፡ እስመ ፡ ኢ.ይደሉ ፡ ይብልዑ ፡ በዕለተ ፡ በዓለ ፡ ሰማዕታት ፡ እመ ፡ ኮነ ፡ በመዋ ዕለ ፡ ጾም ፡ እስመ ፡ እሉስ ፡ ሰማዕታት ፡ ሞቱ ፡ ወውዕዩ ፡ በእሳት ፡ እንዘ ፡ ርኍባን ፡ ወፅሙ አን ።

፩፻፺፭ ወበእንተ ፡ ዕለተ ፡ ልደትሰ ፡ ወጥምቀት ፡ በው እቱ ፡ ዘመን ፡ ዘተጋብኡ ፡ ጉባኤ ፡ በኒቅያ ፡ አዘዙ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ቍርባን ፡ ቦሙ ፡ በሌ ሊት ፡ ወከማሁ ፡ በበዓለ ፡ ፶ኒ ፡ ካዕበ ።

፩፻፺፮ ወበጾመ ፡ ፵ ፡ ቅድስት ፡ በሱባዔ ፡ ቀዳማዊ ፡ ይጼሙ ፡ እስከ ፡ ዕርበተ ፡ ፀሐይ ፡ ወሶበ ፡ ኀለፈ ፡ ይጼሙ ፡ እስከ ፡ ፲ወ፩ዱ ፡ ሰዓት ፡ ወበ መዋዕለ ፡ ሕማማትስ ፡ እስከ ፡ ፀአተ ፡ ኮከብ ፡ ወኢ.ይሠርገዉ ፡ በእሎን ፡ መዋዕላት ።

፩፻፺፯ ወእንበትኒ ፡ ይግድፉ ፡ ሥርጋዌሆን ፡ ወኵሉ ፡ ለለ፩፩ዱ ፡ ይደሉ ፡ ላዕሌሁ ፡ ከመ ፡ ይትዐቀብ ፡ በዕለተ ፡ ጾመ ፡ ፵ ፡ ወሰሙነ ፡ ሕማማት ፡ እስመ ፡ መድኃኒትነ ፡ ወሥርየተ ፡ ኃጢአትነ ፡ በውስቴቶን ። ወውእቱ ፡ ግብር ፡ ውፁእ ፡ እም ሕገ ፡ ሰብሳብ ፡ ከመ ፡ ኢ.ይትላጸቅ ፡ ፩ዱሂ ፡ ውስተ ፡ መንጸፉ ፡ በመዋዕለ ፡ ፵ ፡ ፍጹመ ። አሌ ፡ ሎቱ ፡ ለዘይገብር ፡ ዘንተ ፡ ኃጢአተ ፡ በመ ዋዕለ ፡ ሕማማት ፡ ቅድስት ፡ ወአመሰ ፡ ገበርን ፡ ፈቃዳቲነ ፡ በጾመ ፡ ፵ ፡ ቅድስት ፡ በፍግዓ ፡ አይ ቴኬ ፡ ሀሎ ፡ ፍሥሓነ ፡ ሶበ ፡ ርኢነ ፡ ትንሣኤሁ፡

ባም ፡ ሴትም ፡ በወለደች ፡ ጊዜ ፡ ሰውን ፡ ወደ ፡ መጠጥ ፡ ቤት ፡ መጥራት ፡ አይገባም ።

፩፻፺፫ በስ ፡ ሯ፫ ፡ ከካህናት ፡ ወገን ፡ ማንም ፡ ቢሆን ፡ በ፵ ፡ ጾም ፡ በዓርብና ፡ በረቡዕም ፡ ጾም ፡ ወይን፡ መጠጣት ፡ አይገባውም ፤ ወደ ፡ መዋት ፡ (ውሽ ባ ፡ ቤት ፡) አይግባ ። በዐቢይ ፡ ጾም ፡ ወራት ፡ ሰው ፡ ከሚስቱ ፡ ጋር ፡ አይተኛ ።

፩፻፺፬ የሰማዕታት ፡ በዓል ፡ ከጾም ፡ ላይ ፡ ቢውል ፡ ስለ ፡ ሰማዕታት ፡ ሞት ፡ ምክንያት ፡ ኤጲስቆ ጶሱ ፡ ወይም ፡ ቄሱ ፡ ለሕዝቡ ፡ በመብል ፡ በዓል ፡ ቢያከብር ፡ ይሻር ። እርሱ ፡ ለብዙዎች ፡ ሰዎች ፡ የኃጢአት ፡ ምክንያት ፡ ሆኗልና ፡ እነ ርሱ ፡ በፈቃዳቸው ፡ ቢበሉ ፡ ግን ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ ወይም ፡ ቄሱ ፡ ይለያቸው ። በጾም ፡ ወራት ፡ ከሆነ ፡ በሰማዕታት ፡ በዓል ፡ ቀን ፡ በመብል ፡ በመጠጥ ፡ ማክበር ፡ አይገባቸውምና ። እነዚህ ፡ ሰማዕታት ፡ እየተራቡ ፡ እየተጠሙ ፤ በእሳት ፡ ተቃጥለው ፡ ሞተዋልና ።

፩፻፺፭ ስለ ፡ ልደትና ፡ ስለ ፡ ጥምቀት ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ በኒቅያ ፡ የተሰበሰቡ ፡ ሊቃውንት ፡ ቅዳ ሴው ፡ በሌሊት ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ አዘዙ ። ዳግ መኛም ፡ በበዓለ ፡ ፶ ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ።

፩፻፺፮ ከብርት ፡ በምትሆን ፡ በ፵ ፡ ጾም ፡ በመጀመሪ ያው ፡ ሱባዔ ፡ ፀሐይ ፡ እስኪገባ ፡ ድረስ ፡ ይጹሙ ። የመጀመሪያው ፡ ሱባዔ ፡ ካለፈ ፡ በኋ ላም ፡ እስከ ፡ ፲፩ ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ ይጹሙ ። በሰሙነ ፡ ሕማማት ፡ ግን ፡ ኮከብ ፡ እስኪወጣ ፡ ድረስ ፡ ይጹሙ ። በእነዚህም ፡ ወራቶች ፡ አያ ጊጡ ።

፩፻፺፯ ሴቶችም ፡ ጌጣቸውን ፡ ይተዉ ። ሁሉም ፡ ለእያ ንዳንዱ ፡ በ፵ ፡ ጾምና ፡ በሰሙነ ፡ ሕማማት ፡ መጠበቅ ፡ ይገባዋል ፡ ድኅነታችንና ፡ የኃጢአ ታችን ፡ ሥርየት ፡ በእነርሱ ፡ ነውና ። ይኸውም ሥራ ፡ አንዱስ ፡ እንኳ ፡ በ፵ ፡ ጾም ፡ ወራት ፡ በምንጣፍ ፡ ፈጽሞ ፡ እንዳይገናኝ ፡ ከጋብቻ ፡ ሕግ ፡ የወጣ ፡ ነው ። ክብርት ፡ በምትሆን ፡ በሕማማት ፡ ወራት ፡ ይህችን ፡ ኃጢአት ፡ የሚሠራት ፡ ሰው ፡ ወዮለት ። በ፵ጾም ፡ በተ ድላ ፡ በደስታ ፡ ፈቃዳችንን ፡ ካደረግን ፡ ትን ሣኤውን ፡ ባየን ፡ ጊዜ ፡ ተድላ ፡ ደስታችን ፡ ወዴት ፡ አለ ?

፭፻፶፰ ወእኮ ፡ ጾም ፡ እምኅብስት ፡ ወማይ ፡ እላ ፡ ጾምሰ ፡ ዘውኩፍ ፡ ቅድመ ፡ እግዚእብሔር ፡ ውእቱ ፡ ንጽሐ ፡ ልብ ። ወሶበ ፡ ኮነ ፡ ሥጋ ፡ ርጉበ ፡ ወፅሙአ ፡ ወነፍስሰ ፡ ትበልዕ ፡ እመፍቅዳት ፡ ወልብኒ ፡ ይትፌጋዕ ፡ እምጣዕማት ፡ ምንትኑ ፡ ረባሑ ፡ ለጾምከ ።

፭፻፶፱ ሥርዋጽ ፡ ክርስጣ ፡ ዘ፴ ፡ ፵ ፡ ዕለተ ፡ ይጼሙ ፡ ጾመ ፡ በተፀምዶ ፡ ወበትሕትና ፡ ወይደሉ ፡ ተማኅሥ ፡ እምጥሉላት ፡ ወኢያውስቡ ።

፮፻ ወኢይኩን ፡ በሰሙነ ፡ ሕማማት ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ ወኢሢመተ ፡ ክህነት ፡ ወጸሎተ ፡ አስተብቍዖ ፡ ላዕለ ፡ ምዉታን ፡ እላ ፡ ይደሉ ፡ ተፀምዶ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በእሉ ፡ መዋዕላት ፡ ፍጹመ ። ወዳእሙ ፡ በበዓለ ፡ ሆሣዕና ፡ ይትነበብ ፡ ግንዘተ ፡ ሙታን ፡ ወመጽሐፈ ፡ ሐዋርያት ፡ ወወንጌላት ፡ ወፍትሐታት ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ይመውቱ ፡ በሰሙነ ፡ ሕማማት።

፮፻፩ ወኢይትበሀል ፡ በዕለተ ፡ ሐሙስ ፡ ጸሎተ ፡ ተአምኖ ፡ ወእእግዚእ ፡ ሕያዋን ፡ ወእጸሎተ ፡ ቡራኬ ። ወበዕለተ ፡ ሰንበትሰ ፡ ይትበሀል ፡ እግዚእ ፡ ሕያዋን ፡ ወፍትሐት ፡ ወጸሎተ ፡ ዕጣን ፡ ዘእንበለ ፡ ሰዓም ፡ ወኢይደሉ ፡ ግንዘት ፡ በዕለተ እሑድ ፡ ወኢብካይ ፡ በዕለተ ፡ ፋሲካ ። ወበውስቴታ ፡ ካዕበ ፡ ኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ እመ ፡ ጾም ፡ ምንትኒ ፡ እምትፍሥሕታት ፡ ወኢእውሰቦት ፡ ወኢሢመተ ፡ ክህነት ፡ ወኢጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ ወኢምንትኒ ፡ እምሢመታት ፡ ዘእንበለ ፡ ጸሎት ። በእንተ ፡ ምዉት ፡ ወጥምቀተ ፡ ክርስትናሰ ፡ ለዘይትፈራህ ፡ በእንቲአሁ ፡ ሞት ።

፮፻፪ ሥርዋጽ ፡ ነበረ ፡ ውስተ ፡ ቀኖና ፡ ዘነገሥት ፡ ግብር ፡ ዘበእንተ ፡ ጾም ፡ ዐቢይ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ፰ቱ ፡ ሰሙን ፡ ጥንቱ ፡ ተፍጻሜተ ፡ ክረምት ፡ ይትዐወቅ ፡ እኮ ፡ ክረምተ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወተፍጻሜቱ ፡ ጥንቱ ፡ ለሐጋይ ፡ እመ ፡ ለለኵሉ ፡ ሰሙን ፡ ፭ቱ ፡ ዕለታት ።

፮፻፫ ወይብልዎ ፡ እመ ፡ ሰንበት ፡ በዓለ ፡ ሕግ ፡ ብሉይ ፡ ወእመ ፡ እሑድ ፡ በዓለ ፡ ሕግ ፡ ሐዲስ ፡ ወኢይብልዎ ፡ መቃስግተ ። ወጾመ ፡ ረቡዕሰ ፡ ወዓርብ ፡ ይጼሙ ፡ ወትረ ፡ ዘእንበለ ፡ በዓላት ፡ ወበዓለ ፡ ፶ ።

፮፻፬ ወድልው ፡ ለእግዚእብሔር ፡ ላዕለ ፡ ተእዛዝያ



፭፻፶፰ ጾም ፡ ከእህል ፡ ከውኃ ፡ መከልከል ፡ አይደለም ፡ ከእግዚእብሔር ፡ ፊት ፡ የሚደርስ ፡ ጾምስ ፡ የልብ ፡ ንጽሕና ፡ ነው ። ሥጋ ፡ ቢራብ ፡ ቢጠማ ፡ ነፍስ ፡ ግን ፡ ፈቃዷን ፡ ብትፈጽም ፡ ልብም ፡ ከጣዕሙ ፡ የተነሣ ፡ ደስ ፡ ቢለው ፡ የጾምህ ፡ ጥቅሙ ፡ ምንድን ፡ ነው ?

፭፻፶፱ ሥርዋጽ ፡ ክርስጣ ፡ ፴ ፡ በተባሕትዎ ፡ በትሕትና ፡ ፵ ፡ ቀን ፡ ጾምን ፡ ይጹሙ ። ከጥሉላት ፡ መከልከል ፡ ይገባል ። አያግቡም ።

፮፻ በሰሙነ ፡ ሕማማት ፡ ክርስትና ፡ ማንሳት ፡ ክህነት ፡ መስጠት ፡ ለሞቱ ፡ ሰዎች ፡ መጸለይ ፡ አይገባም ። በእነዚህም ፡ ቀኖች ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ፈጽሞ ፡ ማገልገል ፡ ይገባል ፡ እንጂ ። በሰሙነ ፡ ሕማማት ፡ ስለሚሞቱት ፡ ሰዎች ፡ የሙታን ፡ ግንዘትና ፡ የሐዋርያት ፡ ሥራ ፡ ወንጌላት ፡ የሙታን ፡ ፍታት ፡ በሆሣዕና ፡ በዓል ፡ ቀን ፡ ይነበብ ፡ እንጂ ።

፮፻፩ በጸሎተ ፡ ሐሙስ ፡ ጸሎተ ፡ ተአምኖ ፡ እግዚእ ፡ ሕያዋን ፡ የቡራኬ ፡ ጸሎት ፡ አይባልም ፡ (አይጸለይም) ። ቅዳሜ ፡ ግን ፡ እግዚእ ፡ ሕያዋን ፡ ይባላል ፡ ፍትሐት ፡ ይፈታል ። ከመሳለም ፡ በቀር ፡ ጸሎተ ፡ ዕጣንም ፡ ይጸለያል ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ ግንዘት ፡ ማድረግ ፡ በፋሲካ ፡ ቀንም ፡ ማልቀስ ፡ አይገባም ። ዳግመኛም ፡ በውስጧ ፡ በ፵ ፡ ጾም ፡ ከተድላ ፡ ደስታ ፡ ወገን ፡ ምንም ፡ ማድረግ ፡ አይገባም ። መጋባት ፡ ክህነት ፡ መስጠት ፡ ክርስትና ፡ ማንሣት ፡ ከሹመትም ፡ ወገን ስለሚሞቱት ፡ ከመጸለይ ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ ማድረግ ፡ አይገባም ። ይሞታል ፡ ተብሎ ፡ ለሚያስፈራው ፡ ግን ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ ያደረጉለታል ።

፮፻፪ ሥርዋጽ ፡ ዐቢይ ፡ ጾም ፡ ስምንት ፡ ሱባዔ ፡ እንደሆነ ፡ በነገሥታት ፡ መጽሐፍ ፡ ተጻፈ ፡ መጀመሪያው ፡ የክረምት ፡ መጨረሻ ፡ ነው ። የኢትዮጵያ ፡ ክረምት ፡ እንዳይደለ ፡ ይታወቃል ፡ መጨረሻው ፡ የበጋ ፡ መጀመሪያ ፡ ነው ፡ በየሳምንቱ ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ መጾም ፡ ይገባል ።

፮፻፫ በብሉይ ፡ ሕግ ፡ በዓል ፡ በቅዳሜ ፡ በሐዲስ ፡ ሕግ ፡ በዓል ፡ በእሑድ ፡ ይብሉ ፡ ቅመማት ፡ የበዛበትን ፡ አይብሉ ። የዓርብንና ፡ የረቡዕን ፡ ጾም ፡ ግን ፡ ከልደት ፡ ከጥምቀት ፡ ከበዓለ ፡ ፶ ፡ በቀር ፡ ዘወትር ፡ ይጹሙ ።

፮፻፬ ከእሑድና ፡ ከቅዳሜ ፡ በቀር ፡ ለእግዚእብሔር ፡

ኒሁ ፡ ጾመ ፡ አርድእቲሁ ፡ እምድኅረ ፡ በዓለ ፡ ፶ ፡ ዕለት ፡ ዘእንበለ ፡ ስንበታቲሃ ፡ ወእሑዳቲሃ ።

## አንቀጽ ፡ ፲ወ፯ቱ ።

በእንተ ፡ ምጽዋት ፡

፩፻፳፮ ምጽዋትሰ ፡ ጾታ ፡ ውእቱ ፡ እምጸዋትወ ፡ ምሕረት ፡ ወውእቱ ፡ ተሣህሎቱ ፡ ለሰብእ ፡ በንዋዩ ፡ ላዕለ ፡ እለ ፡ ይፈቅድዎ ፡ እንዘ ፡ ኢየኀሥሥ ፡ ነሢአ ፡ ፍዳ ፡ እምኀቤሆሙ ። እላ ፡ በእንተ ፡ ትእዛዘ ፡ እግዚእነ ፡ ዘይቤ ፡ ሢጡ ፡ ንዋየክሙ ፡ ወሀቡ ፡ ምጽዋተ ፡ ለነዳያን ፡ ወግበሩ ለክሙ ፡ ቍናማተ ፡ ዘኢይበሊ ፡ ወመዝገበ ፡ በሰማያት ፡ ዘኢይማስን ፡ ወኢየኀልፍ ። ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ ሀቡ ፡ ምጽዋተ ፡ ወኵሉ ፡ ይኩውን ፡ ለክሙ ፡ ንጹሐ ።

፩፻፳፯ ወበምጽዋት ፡ ይትሜሰሎ ፡ ብእሲ ፡ ለፈጣሪሁ ፡ በእምጣነ ፡ ዘይትክህሎ ። እስመ ፡ ውሂበ ፡ ምጽዋት ፡ ወተሣህሎ ፡ እምነ ፡ ጠባይዕ ፡ እምላካዊ ፡ ወእግዚእነ ፡ ይቤ ፡ ኩኑ ፡ መሐርያነ ፡ ከመ ፡ አቡክሙ ፡ ሰማያዊ ።

፩፻፳፰ ወምጽዋትሰ ፡ ልቃሕ ፡ እምላካዊት ። ወይእቲ ፡ ካዕበ ፡ ተናግዶ ፡ እምላካዊት ፡ ማእምንት ፡ ረባሒት ፡ ወይእቲ ፡ ዓዲ ፡ ማሕፀንተ ፡ ጠቢብ ፡ ዘያንብራ ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምላኩ ፡ እስከ ፡ ጊዜ ፡ ፈቃዱ ። ወይእቲ ፡ ካዕበ ፡ ቍርባን ፡ ውኩፍት ፡ በኀበ ፡ መቅደስ ፡ ነባቢት ፡ ወእግዚአብሔርኒ ፡ ይትለዐል ፡ ዝክሩ ፡ ይቤ ፡ እፈቅድ ፡ ምጽዋተ ፡ ወእኮ ፡ መሥዋዕተ ።

፩፻፳፱ ወካዕበ ፡ ምስሌሃ ፡ ጾምኒ ፡ ይኩውን ፡ ውኩፈ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ነቢይ ፡ ወምስሌሃ ፡ ጸሎትኒ ፡ ይኩውን ፡ ውኩፈ ፡ በከመ ፡ ተብህለ ፡ በቆርነሌዎስ። ወዘእንበሌሃሰ ፡ ድንግልናሂ ፡ ኢትረብኅ ፡ በከመ ፡ ተጽሕፈ ፡ ለእብዳት ፡ ኃምስ ።

፩፻፴ ወትእዛዛትሂ ፡ ወእምሳላት ፡ ዘተነግራ ፡ በምክንያተ ፡ ዚአሃ ፡ ውስተ ፡ መጻሕፍት ፡ እምላክ

## አንቀጽ ፡ ፲፯ ።

ስለ ፡ ምጽዋት ።

የሚታዘዙ ፡ ሰዎች ፡ ከበዓሊ ፡ ፶ ፡ በኋላ ፡ የሐዋርያትን ፡ ጾም ፡ መጾም ፡ ይገባቸዋል ።

፩፻፳፮ ምጽዋትስ ፡ ከርኅራኄ ፡ ወገን ፡ ነው ፡ ይኸውም ሰው ፡ በገንዘቡ ፡ ምጽዋትን ፡ ለሚሹት ፡ ሰዎች፣ የሚያደርገው ፡ ርኅራኄ ፡ ነው ። ከእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ትርፍ ፡ ሳይሻ ፡ ጌታችን ፡ "ገንዘባችሁን ሽጣችሁ ፡ ለድሆች ፡ ምጽዋት ፡ ስጡ ፡ ብሎ ፡ ስላዘዘ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የማይጠፋ ፡ ኮረጆ ፡ አድርጉ ፡ የማይጠፋ ፡ የማያልፍ ፡ ሰማያዊ ፡ ድልብ ፡ አከማቹ ።" (ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፴፫) ፡ ዳግመኛም ፡ ጌታችን ፡ ምጽዋትን ፡ ስጡ ፡ ሁሉም ፡ ንጹሕ ፡ ይሆንላችኋል ፡ አለ ።

፩፻፳፯ ሰው ፡ በምጽዋት ፡ በሚቻለው ፡ መጠን ፡ ፈጣሪውን ፡ ይመስለዋል ። ምጽዋትና ፡ መራራት ፡ ከእምላክ ፡ የተገኘ ፡ ባሕርይ ፡ ነውና ። ጌታችንም ፡ "እንደሰማያዊ ፡ አባታችሁ ፡ የምትራሩ ፡ ሁኑ ፡ አለ ። (ማቴ ፡ ፭ ፡ ፵፰) ።

፩፻፳፰ ምጽዋትስ ፡ እምላካዊት ፡ ብድር ፡ ናት ። ይህችውም ፡ የታመነችና ፡ የምትረባ ፡ እምላካዊት ፡ ንግድ ፡ ናት ። ይዘችውም ፡ ዳግመኛ ፡ ወዶ ፡ እስኪወስዳት ፡ ድረስ ፡ ብልህ ፡ ሰው ፡ ከፈጣሪው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የሚያኖራት ፡ አደራ ፡ ናት ። ይህችውም ፡ ዳግመኛ ፡ በነባቢት መቅደስ ፡ ዘንድ ፡ ተቀባይነት ፡ ያላት ፡ ቍርባን ፡ ናት ። እግዚአብሔርም ፡ ስም ፡ አጠራሩ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይበልና ፡ መሥዋዕትን ፡ ያይደለ ፡ ምጽዋትን ፡ እሻለሁ ፡ አለ " (ሆሴዕ ፡ ፮ ፡ ፮ ፡ ማቴ ፡ ፱ ፡ ፲፫) ።

፩፻፳፱ ዳግመኛም ፡ ከእርሱዋ ፡ ጋር ፡ ጾም ፡ ተቀባይነት ፡ ያለው ፡ ይሆናል ። ነቢዩ ፡ እንደተናገረ ፡ (ኢሳ ፡ ፶፰ ፡ ፮- ፯) ጸሎትን ከርሷ ፡ ጋር ፡ ይቀበላል ፡ በቆርነሌዎስ ፡ እንደተናገረ ። ያለርሷ ፡ ግን ፡ ድንግልናም ፡ አትጠቅምም ፡ በአምስቱ ፡ ሰነፎች ፡ ደናግል ፡ እንደተጻፈ" (ማቴ ፡ ፳፭ ፡ ፩ - ፲፪) ።

፩፻፴ በምጽዋት ፡ ምክንያት ፡ ትእዛዞችና ፡ ሕጎችም ፡ የእምላክን ፡ ነገር ፡ በሚናገሩ ፡ መጻሕፍት ፡

ውዖት ፡ ብዙኃት ፡ ጥቀ ። ወበእንቲአሁ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ ለዘሰአለከ ፡ ሀብ ። ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ ብፁዓን ፡ መሐርያን ፡ እስመ ፡ ሎሙ ፡ ይምሕርዎሙ ። ወብሂሎቱኒ ፡ ለመሐርያን ፡ ሑሩ ፡ ኅበ ፡ መንግሥት ፡ ዘድልው ፡ ለክሙ ፡ እምቅድመ ፡ ይትፈጠር ፡ ዓለም ። ወብሂሎቱ ፡ ለጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ኢትርስዑ ፡ ምሕረተ ፡ ነዳያን ፡ ወተሳተፍዎሙ ፡ እስመ ፡ በእምሳለ ፡ ዝንቱ ፡ መሥዋዕት ፡ ያሠምሮ ፡ ብእሲ ፡ ለእግዚአብሔር ።

፮፻፲ ወበቍዔታስ ፡ ለምጽዋት ፡ በብዙኅ ፡ ኀጺት ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆ ፡ ይእቲ ፡ ትደልዎሙ ፡ ለአብዕልት ፡ ወለነዳያን ፡ ዙሉ ፡ ለለ፩ዱ ፡ ከመ ፡ የሀቡ፡ በእምጣነ ፡ ከሂሎቶሙ ፡ ወዕሤታኒ ፡ በአምጣነ ፡ ጸሀቀ ፡ ወሃቢሃ ፡ እመኒ ፡ በብዙኅ ፡ ወእመኒ ፡ በኅዳጥ ፡ ወለአብዕልትሰ ፡ ዘከመ ፡ ባህሉ፡ ለልዑል ፡ ዘአማኀፀንዎ ፡ ብዙኀ ፡ ይትኃሠሥዎ፡ ብዙኀ ።

፮፻፲፩ ወብሂሎቱ ፡ ለዘአፍቀረኒ ፡ ብዙኀ ፡ ይትኀደግ ፡ ሎቱ ፡ ብዙኀ ፡ ወብሂሎቱ ፡ ሀቡ ፡ ወይሁቡ ከሙ ፡ መሰፈርተ ፡ ምሉእ ፡ ወትሩፈ ፡ ወናደፈደ ፡ ውስተ ፡ ሕፅንክሙ ፡ እስመ ፡ በመስፈርት ፡ ዘሰፈርክሙ ፡ ይሰፍሩ ፡ ለክሙ ። ወጳውሎስኒ ፡ ሐዋርያሁ ፡ ተለወ ፡ በዝንቱ ፡ ቃለ ፡ እግዚኡ ፡ ወይቤ ፡ ዘሰ ፡ ይዘርእ ፡ በሕጸጽ ፡ በሕጸጽ ፡ የዐጽድ ፡ ወዘሰ ፡ ይዘርእ ፡ በበረከት ፡ በበረከት ፡ የእርር ፡ ወዙሉ ፡ ብእሲ ፡ ዘከመ ፡ ይሔሊ ፡ በልቡ ፡ ይገብር ።

፮፻፲፪ ጤት ፡ ፲ወ፯ቱ ፡ አዝዘሙ ፡ ለአብዕልተ ፡ ዝንቱ፡ ዓለም ፡ ከመ ፡ ኢይትዓበዩ ፡ በልቦሙ ፡ ወይኩኑ ፡ ፍሡሐነ ፡ በውሂብ ፡ ወተአዝዞ ፡ ከመ ፡ ያንብሩ ፡ ለነፍሳቲሆሙ ፡ መሠረተ ፡ ሠናየ ፡ ለግብር ፡ ዘሀለወ ፡ ይምጻእ ። ወበእንተ ፡ ነዳያንኒ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ ልዑል ፡ ሶበ ፡ አብአት ፡ ብእሲት ፡ ፪ተ ፡ ጸራይቀ ፡ እስመ ፡ ይእቲ ፡ አብአት ፡ ዙሎ ፡ ሕይወታ ፡ ወካልእንሰ ፡ አብኡ እምተረፎሙ ። ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ "ዘአስተየክሙ ፡ ጽዋዐ ፡ ማይ ፡ ቈሪር ፡ በስምየ ፡ እስመ ፡ እለ ፡ ክርስቶስ ፡ አንትሙ ፡ አማን ፡ እብለክሙ ፡ ኢየኀጕል ፡ ዕሤቶ" ።



እጅግ ፡ የተነገሩ ፡ ናቸው ፡ ስለርሷም ፡ ጌታችን ፡ "ስለመነህ ፡ ስጠው ፡ አለ" (ማቴ ፡ ፭ ፡ ፵፪) ። ዳግመኛም ፡ የሚራሩ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው፡ አለ ፡ ለእነርሱም ፡ ይራሩላቸዋልና ።" (ማቴ ፡ ፭ ፡ ፯) ለሚራሩ ሰዎች ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ ወደተዘጋጀላችሁ ፡ ወደ ፡ መንግሥት ፡ ስማያት ግቡ ፡ ማለቱ ፡ ሐዋርያው ፡ ጳውሎስም ፡ ለድሆች ፡ ምጽዋትን ፡ መስጠትን ፡ አትዘንጉ ምስሏቸውም ፡ ማለቱ ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ መሥዋዕት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ ያሰኘዋልና ፡ ነው" (ዕብ ፡ ፲፫ ፡ ፲፮) ።

፮፻፲ የምጽዋት ፡ ጥቅሟ ፡ በብዙ ፡ ወገን ፡ ነው ፡ ከነርሱም ፡ አንዱ ፡ ሁሉም ፡ ለእየንዳንዱ ፡ እንደችሎታቸው ፡ መጠን ፡ ምጽዋትን ፡ ይሰጡ ፡ ዘንድ ለባለጸጎቹና ፡ ለድሆቹም ፡ ትገባቸዋለች ። ዋጋዋም ፡ እንደ ፡ ሰጭዋ ፡ ትጋት ፡ መጠን ፡ ነው ፡ በብዙም ፡ ቢሆን ፡ በጥቂትም ፡ ቢሆን ። ለባለጸጎችስ ፡ ጌታችን ፡ በብዙ ፡ ያስጠበቁትን ፡ ሰው ፡ በብዙ ፡ ይመረመሩታል" (ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፵፰) ብሎ ፡ እንደተናገረው ፡ ነው ።

፮፻፲፩ ብዙ ፡ ለወደደኝም ፡ ብዙ ፡ ይሠረይለታል ፡ ማለቱ ፡ ስጡ ፡ ስፍረው ፡ መልተው ፡ አትርፈውም ፡ ይሰጧችኋል ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ ይልቁንም ፡ በሥራችሁ ፡ በስፈራችሁበት ፡ መስፈሪያ ፡ ይሰፍሩላችኋልና" (ሉቃ ፡ ፯ ፡ ፵፯ ፡ ማር ፡ ፬ ፡ ፳፬) ። ሐዋርያው ፡ ጳውሎስም ፡ በዚህ ፡ የጌታውን ፡ ቃል ፡ ተከተለ ፡ "በጥቂቱ የዘራ በጥቂቱ ፡ ያጭዳል ፡ በብዙ ፡ የዘራ ፡ በብዙ ፡ ይሰበስባል ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በልቡ ፡ የሚያሰበውን ፡ ያድርግ ፡ አለ" ። (፪ኛ ፡ ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፮)

፮፻፲፪ ጤት ፡ ፲፯ ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ባለጸጎች ፡ በልባቸው ፡ እንዳይታበዩ ፡ እዘዛቸው ፡ በመስጠት ፡ በመታዘዝ ፡ ደስተኞች ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ይመጣ ዘንድ ፡ ላለው ፡ ክብር ፡ ለሰውነታቸው ፡ በጎ ፡ መሠረት ፡ ይመሠረቱ ፡ ዘንድ ፡" (፩ኛ ፡ ጢሞ ፡ ፮ ፡ ፲፯) ። ስለ ፡ ድሆችም ፡ ልዑል ፡ ጌታችን ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ሁለት ፡ ጸሪቅ ፡ ባገባች ፡ ጊዜ ፡ "ይህች ፡ ያላትን ፡ ገንዘቧን ፡ ሰጥታለችና ፡ ሌሎቹ ፡ የተረፋቸውን ፡ አገቡ ፡ አለ" (ማር ፡ ፲፪ ፡ ፵፪ - ፵፫) ። ዳግመኛም ፡ "የክርስቶስ ፡ ወገኖች ፡ ናችሁ ፡ ብሎ ፡ በስሜ ፡ ቀዝቃዛ ፡ ጽዋ ያጠጣችሁ ፡ ዋጋውን ፡ አያጣም ፡ ብዬ ፡ እነግራችኋለሁ ፡ አለ" (ማር ፡ ፱ ፡ ፵፩) ።

አንቀጽ ፲፮ ።

፮፻፲፫ ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ እግዚእብሔር ፡ ልዑል ፡ በልሳነ ፡ ኢሳይያስ ፡ ነቢይ ፡ ክፍል ፡ ኅብስተከ ፡ ማእከሌከ ፡ ወማእከለ ፡ ርኁባን ።

፮፻፲፬ ወዓዲ ፡ ይቤሉ ፡ ሐዋርያት ፡ በዲድስቅልያ ፡ ዘ፲፮ቱ ፡ አፍቅሮ ፡ ለእግዚእብሔር ፡ በንዋይከ ፡ ዘወሀበከ ፡ ኪያሁ ፡ በእምጣነ ፡ ክሂሎትከ ፡ ወዘትክል ፡ በጎቢሁ ፡ ደዮ ፡ ውስተ ፡ ሙዳየ ፡ ምጽዋት ፡ ወለእመኒ ፡ ፩ደ ፡ ጸሪቀ ፡ እበ ፡ ፪ተ ፡ እው ፡ ፫ተ ፡ ወእመ ፡ ትፈቅድ ፡ ትትእዘዝ ፡ ተሳተፎሙ ፡ ለእናግድ ፡ በንዋይከ ።

፮፻፲፭ ዘ፳ወ፩ዱ ፡ ወበእንተ ፡ ኅብስትስ ፡ ዘይትወሀብ ፡ እምድኅረ ፡ መበለታት ፡ ውእቱ ፡ ኅሩይ ፡ በጽድቅ ፡ ወለእመኒ ፡ ኅዳጥ ፡ ውኩፍ ፡ ውእቱ ።

፮፻፲፮ ዘ፳ወ፫ቱ ፡ ወዘእልቦቱ ፡ ምንትኒ ፡ ይጹም ፡ ወይረሲ ፡ መንፈቀ ፡ ኅብስቱ ፡ ለቅዱሳን ።

፮፻፲፯ ወዓዲ ፡ እስመ ፡ ምጽዋት ፡ እንተ ፡ ተሠርዐት ፡ ኀበ ፡ ፪ቱ ፡ ትትከፈል ፡ በኅቡእ ፡ ወበገሃድ ፡ እምእደዊሁ ፡ ለዘይመጸውት ፡ ለጽኑሳን ፡ ወለርኁባን ፡ ወሰሙኣን ፡ ወሰሩቃን ፡ ወለነግድ ፡ ወለድውያን ፡ ወሙቁሓን ፡ ወለእለሂ ፡ ተሰዱ ። በከመ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ዳሰሙ ይኩን ፡ ምጽዋትከ ፡ በኅቡእ ፡ ወአቡከ ፡ ዘይሬእየከ ፡ በኅቡእ ፡ የዐሥየከ ፡ ክሡተ ። ወበእንተ ፡ ዘይቤሎሙ ፡ በዕለተ ፡ ፍትሕ ፡ ለእለ ፡ ይቀውሙ ፡ በየማኑ ።

፮፻፲፰ ወበከመ ፡ ይቤ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያሁ ። ሰብ ፡ ዘ፲ቱወ፫ ፡ ወእትርስዑ ፡ ተቀብሎተ ፡ ነግድ ፡ እስመ ፡ በእንቲአሁ ፡ ቦ ፡ እለ ፡ ከፈሎሙ ፡ እንዘ ፡ ኢየእምሩ ፡ ከመ ፡ ይትቀበሉ ፡ ነግደ ፡ መላእክት ፡ ተዘከሩ ፡ ሙቁሓነ ፡ ዘከመ ፡ ተሞቃሕክሙ ፡ ምስሌሆሙ ።

፮፻፲፱ ወዘገሃድስ ፡ ይእቲ ፡ ዘይፀውሩ ፡ ዘይመጸውት ፡ ኀበ ፡ ካህን ፡ ሥዩም ፡ ወይእቲ ፡ ዓሥራት ፡ ወበኵር ፡ ወብፅዓት ፡ በከመ ፡ ቃለ ፡ ሐዋርያት ፡ ዘይቤሉ ።

፮፻፳ ድስቅ ፡ ፰ቱ ፡ ዓሥራትስ ፡ ወበኵር ፡ ወብፅዓት ፡ ዘይወስድዎሙ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በከመ ፡ አዘዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክፍልዎሙ ፡ ለእግብርተ ፡ እግዚእብሔር ።
ወእንተስ ፡ ያመጽእዋ ፡ ለነዳያን ፡ ይመግቡ ፡ ባቲ ፡ መገብት ፡ ኄራን ፡ ዘይክፍልዋ ፡ ለእጓለ ፡

ስለ ምጽዋት ።

፮፻፲፫ ዳግመኛም ፡ ልዑል ፡ እግዚእብሔር ፡ በነቢዩ ፡ በኢሳይያስ ፡ እንደበት ፡ "ምግብህን ፡ በእንተና ፡ በተራቡት ፡ መካከል ፡ ክፍለህ ፡ ስጥ ፡ አለ" (ኢሳ ፡ ፶፰ ፡ ፯) ።

፮፻፲፬ ዳግመኛም ፡ ሐዋርያት ፡ በዲድስቅልያ ፡ በ፲፮ኛው ፡ አንቀጽ ፡ በተቻለህ ፡ መጠን ፡ ገንዘብ ፡ የሰጠህን ፡ እግዚእብሔርን ፡ ውደደው ፡ አሉ ፡ የምትችለውንም ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ ጸሪቅ ፡ ቢሆን ፡ ከሙዳየ ፡ ምጽዋት ፡ ጨምረው ፡ አሉ ፡ ልትታዘዝ ፡ ብትወድም ፡ በገንዘብህ ፡ እንግዶችን ፡ ምስላቸው ።

፮፻፲፭ ሸ፩ ፡ ከመበለቶች ፡ ድኅም ፡ የተነሣ ፡ የሚሰጠው ፡ እንጀራ ፡ ግን ፡ በእውነት ፡ የተመረጠ ፡ ነው ፡ ምንም ፡ ትንሽ ፡ ቢሆን ፡ እግዚእብሔር ፡ ይቀበለዋል ።

፮፻፲፮ ሸ፫ ፡ ምንም ፡ የሌለው ፡ ይጹም ፡ የምሳውንም ፡ ግማሽ ፡ ለድሆች ፡ ይስጥ ።

፮፻፲፯ ዳግመኛም ፡ የታዘዘችው ፡ ምጽዋት ፡ ከሁለት ፡ ወገን ፡ ትከፈላለችና ። ከሚመጸውት ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ በስውርና ፡ በግልጥ ፡ ለተቸገሩ ፡ ለተራቡ ፡ ለተጠሙ ፡ ለተራቆቱ ፡ ለእንግዶች ፡ ለሕመምተኞች ፡ ለታሰሩት ፡ ለተሰደዱት ፡ ትከፈላለች ። ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባውና ፡ ጌታችን ፡ "ምጽዋትህ ፡ በስውር ፡ ብቻ ፡ ይሁን ፡ በስውር ፡ የሚያይህ ፡ አባትህ ፡ ገልጦ ፡ ዋጋህን ፡ ይሰጣሃል ፡ እንዳለ (ማቴ ፡ ፮ ፡ ፲-፬) በፍርድ ፡ ቀንም ፡ በቀኙ ፡ የሚቆሙትን ፡ ስለሚላቸው ፡ ነው ።

፮፻፲፰ ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ ሰብ ፡ ፲፫ ፡ እንግዳ ፡ መቀበልን ፡ አትተዉ ፡ ብሎ ፡ እንደተናገረ ። እንግዳ ፡ በመቀበላቸው ፡ ሳያውቁ ፡ መላእክትን ፡ እንግድነት ፡ ይቀበሉ ፡ ዘንድ ፡ ደደላቸው፡ አሉና ። የታሰሩትንም ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ እንደ ታሰራችሁ ፡ ሁናችሁ ፡ አስቡ ።

፮፻፲፱ በግልጥስ ፡ የሚመጸውት ፡ ሰው ፡ ወደተሾመው ካህን ፡ የሚወስዳት ፡ ናት ። ይህችውም ፡ ዓሥራት ፡ በኵራት ፡ ስዕለት ፡ ናት ፡ ሐዋርያት ፡ እንደተናገሩ ።

፮፻፳ ድስቅ ፡ ፰ ፡ አሥራት ፡ በኵራት ፡ ስዕለት ፡ ግን፡ ወደቤተክርስቲያን ፡ የሚወስዷቸው ፡ ናቸው ። እግዚእብሔር ፡ እንዳዘዘ ፡ ለእግዚእብሔር ፡ አገልጋዮች ፡ ያካፍሏቸው ። ድኃን ፡ ሹማምት ፡ ያስተዳድሩበት ፡ ዘንድ ፡ ለነዳያን ፡ የሚያመጡትን ፡ ገንዘብ ፡ ግን ፡ እናት ፡ አባት ፡ ለሞተባ

ማውታ ፡ ወዕቤራት ፡ ወምንዱባን ፡ ወእናግድሂ ፡ እለ ፡ ቦሙ ፡ ተጽናስ ፡ ከመ ፡ ዘይትሐስቦሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንቲአሁ ። እስመ ፡ ውእቱ ፡ ዘረስየ ፡ ዘንተ ፡ ምግብና ፡ በእደዊሆሙ ፡ ከመ ፡ ይክፍሉ ፡ ለጽኑሳን ፡ በጽድቅ ፡ ወኢታማስኑ ፡ ንዋየ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢትብልዕዎ ፡ ወኢትዝርውዎ ፡ ለፈቃድክሙ ፡ በባሕቲትክሙ ፡ ዳእሙ ፡ መማብዎሙ ፡ ቦቱ ፡ ለጽኑሳን ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ለክሙ ፡ ፍኖተ፡ ርቱዐ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ።

፲፻፹፩ ዘ፰ ፡ ስምዑ ፡ ዘተብህለ ፡ ቀዲሙ ፡ ወንሕነኒ ፡ ናሁ ፡ ንደግም ፡ ነጊሮተክሙ ፡ ኪያሁ ፡ ብፅዓት ፡ ወዓሥራት ፡ ወበኵራት ፡ ዘሠርዑ ፡ ቅድመ ፡ ለሊቀ ፡ ካህናቲሁ ፡ ለክርስቶስ ፡ ወለእለ ፡ ይትለእክዎ ፡ ወይእዜኒ ፡ በኵራት ፡ ወዓሥራት ፡ ወብፅዓት ፡ እንተ ፡ ይደልወክሙ ፡ ተሀቡ እምጽእዎ ፡ ኀቤሁ ፡ ካዕበ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ የአምሮሙ ፡ ለምንዱባን ፡ ወይሚግቦሙ ፡ በኵሉ ፡ ለለ፩ዱ ፡ ፩ዱ ፡ በከመ ፡ ይደሉ ፡ ሎቱ ፡ ዘውእቱ ፡ ካህን ፡ ዘተሠይመ ፡ ከመ ፡ ኢይንማእ ፡ ፩ዱ ፡ ፪ተ ፡ ጊዜያተ ፡ እው ፡ ብዙኀ ፡ ጊዜያተ ፡ በ፩ዱ ፡ ዕለት ፡ ወበ፩ዱ ፡ ሱባዔ ፡ ወኢይትረከብ ፡ ካልእ ፡ ዘኢነሥአ ፡ ምንተኒ ፡ ግሙራ።

፲፻፹፪ ዘ፰ ፡ ወቀዳምያተ ፡ እክልክሙ ፡ ወተግባረ ፡ እደዊክሙ ፡ አምጽኡ ፡ ኀቤሁ ፡ በእንተ ፡ በረከት ፡ ከመ ፡ ይባርክ ፡ ላዕሌክሙ ፡ ወሀብዎ ፡ በኵራቲክሙ ፡ ወዓሥራቲክሙ ፡ ወብፅዓታቲክሙ ፡ ወእምኀቲክሙ ፡ ወእምፍሬ ፡ ዘቀደመ ፡ ወእምወይን ፡ ወእምዘይት ፡ ወእምፍሬያት ፡ ወእምፀምር ፡ ወእምኵሉ ፡ ንዋይ ፡ ዘጸገወክሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኪያሁ ። እስመ ፡ ውእቱ ፡ ካህነ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ቍርባንክሙ ፡ ውኩፈ ፡ ወዕጣንክሙ ፡ ሠናየ ፡ ለእግዚአብሔር እምላክክሙ ፡ ወውእቱ ፡ ይባርክ ፡ ተግባረ ፡ እደዊክሙ ፡ ወያፈድፍድ ፡ ለክሙ ፡ ሠናያተ ፡ ምድር ፡ ጥቀ ።

፲፻፹፫ እስመ ፡ በረከት ፡ ትሄሉ ፡ ላዕለ ፡ ርእስ ፡ ዘይሁብ ፡ ምጽዋተ ፡ ወበእንተዝ ፡ እስመ ፡ ምጽዋት ፡ ድልው ፡ ለሰብእ ፡ እምሰብእ ። ወለእመኒ ፡ ኮነት ፡ ብውሕተ ፡ ለኵሉ ፡ ዘይፈቅዳ ፡ ወባሕቱ ፡ ይደልዎ ፡ ቅድመ ፡ ለዘቦቱ ፡ ዕጸበ ፡ ረቀ ፡ ዘከመ ፡ ሰማዕታት ፡ ወእምዝ ፡ ለካህ



ቸው ፡ ለባልቴቶቹ ፡ ለተቸገሩት ፡ ችግር ፡ ላለባቸው ፡ ለእንግዶችም ፡ ከፍለው ፡ ይስጧቸው ፡ በእርሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲቆጣጠራቸው ፡ እርሱ ፡ ይህን ፡ ሹመት ፡ በእጃቸው ፡ ያደረገ ፡ ለተቸገሩት ፡ ስዎች ፡ በእውነት ፡ ከፍለው ፡ ይሰጡ ፡ ዘንድ ፡ ነውና ። የቤተ ፡ እግዚአብሔርን፡ ገንዘብ ፡ እታጥፉ ፡ አትብሉት ፡ ፈቃዳችሁን ፡ ለመፈጸም ፡ ብቻ ፡ አትበትኑት ። በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የቀና ፡ መንገድ ፡ ይሆንላችሁ ፡ ዘንድ ፡ የተቸገሩትን ፡ ሰዎች ፡ አስተዳድሩበት ፡ እንጂ ።

፲፻፹፩ ፰ ፡ አስቀድሞ ፡ የተባለውን ፡ ስሙ ፡ እኛም ፡ ዳግመኛ ፡ እነሆ ፡ ስዕለት ፡ አሥራት ፡ ለክርስቶስ ፡ አገልጋዮች ፡ ለካህናት ፡ አለቃ ፡ አስቀድሞ ፡ የታዘዘላቸውን ፡ በኵራት ፡ ለሚያገለግሉትም ፡ አስቀድሞ ፡ የታዘዘላቸውን ፡ እርሱን ፡ እንነግራችኋለን ። ዛሬም ፡ ልትሰጡት ፡ የሚገባችሁን ፡ ስዕለት ፡ በኵራት ፡ አሥራት ፡ ዳግመኛ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ አምጡት ፡ የተቸገሩትን ፡ እርሱ ፡ ያውቃቸዋልና ፡ ይኸውም ፡ የተሾመው፡ ካህን ፡ ነው ፡ ለእርሱ ፡ እንደሚገባው ፡ ሁሉን ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ይመግባቸው ፡ አንዱ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በአንድ ፡ ቀን ፡ በአንድ ፡ ሳምንት ፡ እንዳይቀበል ፡ ፈጽሞ ፡ ምንም ፡ ያልተቀበለ ፡ ሌላም ፡ እንዳይገኝ ።

፲፻፹፪ ፰ ፡ የእህላችሁን ፡ መጀመሪያ ፡ የእጃችሁን ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ በረከት ፡ ወደእርሱ ፡ አምጡ ፡ ይባርካችሁ ፡ ዘንድ ፡ አሥራታችሁን ፡ በኵራታችሁን ፡ ስዕለታችሁን ፡ እጅ ፡ መንሻችሁን ፡ መጀመሪያ ፡ የደረሰውን ፡ እህል ፡ ከወይኑ ፡ ከዘይቱ ፡ ከፍሬ ፡ ፍሬው ፡ ከጸምሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰጣችሁ ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ ለእርሱ ፡ ስጡት ። እርሱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገልጋይ ፡ ነውና ፡ መሥዋዕታችሁን ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ ዕጣናችሁም ፡ ለአምላካችሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያማረ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ። እርሱም ፡ የእጃችሁን ፡ ሥራ ፡ ይባርክላችኋል ፡ የምድሩንም ፡ ፍሬ ፡ እጅግ ፡ ያበዛላችኋል ።

፲፻፹፫ በረከት ፡ በሚመጸውት ፡ ሰው ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ትኖራለችና ፡ ስለዚህ ፡ ምጽዋት ፡ ከሰው ፡ ወገን ለሰው ፡ ይገባልና ። ምንም ፡ ለሚሻት ፡ ሁሉ ፡ የምትገባ ፡ ብትሆን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የፈቃድ ፡ ጭንቅ ፡ ላለው ፡ ሰው ፡ አስቀድሞ ፡ መስጠት ፡ ይገባል ። እንደሰማዕታት ፡ ላሉ ፡ ቀጥሎም ፡ ለካህ

ናት ፡ ወእምዝ ፡ ለአዝማድ ፡ ምእመናን ፡ ወእምዝ ፡ ለኵሎሙ ፡ ምእመናን ፡ ወእምዝ ፡ ለኢምእመናን ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ሐዋርያ ።

፩፻፶፬ ድስቅ ፡ ፲ወ፬ቱ ፡ ወለእመ ፡ ኮነት ፡ መበለት ፡ ዘትከል ፡ ትብቋዕ ፡ ለርእሳ ፡ ኢኮነት ፡ መበለተ ። ወእመሰ ፡ ኮነት ፡ ጽንስተ ፡ በእንተ ፡ ደዌሃ ፡ አው ፡ በእንተ ፡ ሐዒነ ፡ ደቂቅ ፡ አው ፡ በእንተ ፡ ድካመ ፡ ኀይለ ፡ ሥጋሃ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ስፋሕ ፡ እዴከ ፡ ኀበ ፡ ዛቲ ፡ ፈድፋደ ።

፩፻፶፭ ዘ፳ወ፫ቱ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘይሁብ ፡ ንዋየ ፡ ለነዳያን ፡ በእእምሮተ ፡ ኄሩት ፡ ይከውን ፡ ፍጹመ ፡ ወዘሰ ፡ ይሁብ ፡ ንዋየ ፡ በእንተ ፡ ሰማዕታት ፡ ይከውን ፡ ፍጹመ ፡ ፈድፋደ ።

፩፻፶፮ ጤት ፡ ፺ቱ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ለምእመናን ፡ ሰቢራት ፡ ለይጸግውዎን ፡ ከመ ፡ ኢይኩና ፡ ከበደ ፡ ላዕለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወባሕቱ ፡ የአከላ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እለ ፡ በእማን ፡ ሰቢራት ።

፩፻፶፯ ወለቀሳውስትኒ ፡ እለ ፡ ያሤንዩ ፡ ግብሮሙ ፡ ያመክዕቡ ፡ እከብሮቶሙ ፡ ወፈድፋደሰ ፡ ለእለ ፡ ይጸምዉ ፡ በቃል ፡ ወበትምህርት ።

፩፻፶፰ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ለእመ ፡ ሀለወ ፡ ፩ዱ ፡ ዘቦቱ ፡ አዝማድ ፡ ወፈድፋደሰ ፡ እመ ፡ ኮኑ ፡ እምሰብእ ፡ ሃይማኖት ፡ ለእመ ፡ ኢጽሕቀ ፡ በዘይሤንዮሙ ፡ ናሁ ፡ ክሕደ ፡ ሃይማኖቶ ፡ ወውእቱ ፡ የአኪ ፡ እምእለ ፡ ኢየአምኑ ።

፩፻፶፱ ዘገላትያ ፡ ፺ቱ ፡ ወይእዜኒ ፡ እምጣነ ፡ ብነ ፡ መዋዕል ፡ ንግበር ፡ ሠናየተ ፡ ለኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ወፈድፋደሰ ፡ ለሰብእ ፡ ሃይማኖት ። ምጽዋትሰ፡ ይደሉ ፡ ለኵሉ ፡ ዘተጸነሰ ፡ እመኒ ፡ እማኒ ፡ እው ፡ ከሐዲ ፡ እመኒ ፡ ሠናይ ፡ አው ፡ እኩይ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ ለኵሉ ፡ ዘሰእለከ ፡ ሀቦ ፡ ወኢትምትሩ ፡ ተስፋሁ ፡ ለ፩ዱሂ ። ወኩኑ፡ ፍጹማነ ፡ ከመ ፡ አቡክሙ ፡ ሰማያዊ ፡ ዘያዘንም ፡ ዝናመ ፡ ላዕለ ፡ ጸድቃን ፡ ወዐማፅያን ።

፩፻፷ ድስቅ ፡ ፲ወ፫ቱ ፡ ሀብዎሙ ፡ ለጽኑሳን ፡ ወለእመ ፡ ኢኮኑ ፡ መለያልየ ፡ ለክርስቶስ ፡ ወበእንተዝ ፡ እስመ ፡ ተዓቅቦ ፡ ላዕለ ፡ ምጽዋት ፡



ናት ፡ ቀጥሎም ፡ ምእመናን ፡ ለሆኑ ፡ ዘመዶች ፡ ከዚህም ፡ ቀጥሎ ፡ ለምእመናን ፡ ሁሉ ፡ ቀጥሎም ፡ ላላመኑት ፡ ሁሉ ፡ ሐዋርያው ፡ እንደተናገረ (ገላ ፡ ፮ ፡ ፲) ።

፩፻፶፬ ድስቅ ፡ ፲፬ ፡ መበለትዋ ፡ ራሷን ፡ መርዳት ፡ የማቻላት ፡ ከሆነ ፡ ድሀ ፡ አይደለችም ። በደዌ ፡ ምክንያት ፡ የተቸገረች ፡ ወይም ፡ ልጆችዋን ፡ ለማሳደግ ፡ ባትችል ፡ ወይም ፡ የሥጋዋ ፡ ኃይል፡ ደካማ ፡ ቢሆን ፡ ስለዚህ ፡ ወደርሷ ፡ በበለጠ ፡ እጅህን ፡ ዘርጋ ።

፩፻፶፭ ፳፫ ፡ ቸርነትን ፡ በማወቅ ፡ ለድሆቹ ፡ ገንዘቡን ፡ የሚሰጥ ፡ ቢሆን ፡ ፍጹም ፡ ይሆናል ። ይልቁንም ፡ ለሰማዕታት ፡ ገንዘቡን ፡ የሚሰጥ ፡ ሰው ፡ እጅግ ፡ ፍጹም ፡ ይሆናል ።

፩፻፶፮ ጤት ፡ ፰ ፡ ከምእመናን ፡ ውስጥ ፡ ባልቴቶች ፡ ቢኖሩ ፡ ይርዷቸው ። የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሸክም ፡ እንዳይሆኑ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በእርግጥ ፡ ባልቴቶች ፡ የሆኑትን ፡ መርዳት ፡ ለቤተ ፡ ክርርስቲያን ፡ ይበቃታል ።

፩፻፶፯ በጎ ፡ አገልግሎትን ፡ ለሚያገለግሉ ፡ ቀሳውስትም ፡ እጥፍ ፡ ድርብ ፡ አድርገው ፡ ይስጧቸው ፡ ይልቁንም ፡ በቃል ፡ በመናገር ፡ በመጽሐፍ ፡ በማስተማር ፡ ለሚደክሙት ።

፩፻፶፰ ደግመኛም ፡ ዘመዶች ፡ ያሉት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ይልቁንም ፡ ከሃይማኖት ፡ ሰዎች ፡ ውስጥ ፡ ቢሆኑ ፡ ሊረዱ ፡ በሚገባቸው ፡ ገንዘብ ፡ ባይተጋ ፡ እነሆ ፡ ሃይማኖቱን ፡ ካደ ፡ አለ ። ከማያምኑም ፡ ሰዎች ፡ እርሱ ፡ ይከፋል ፡ አለ ። (፩ኛ ፡ ጢሞ ፡ ፭ ፡ ፰)

፩፻፶፱ ገላትያ ፡ ፮ ፡ ዛሬ ፡ ጊዜ ፡ ሳለን ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ በጎ ፡ እናድርግ ፡ (እንሥራ) ፡ ይልቁንም ፡ ለሃይማኖት ፡ ሰዎች ፡ ምጽዋት ፡ ግን ፡ ለተቸገረ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይገባል ፡ አማኒም ፡ ቢሆን ፡ ከሐዲም ፡ ቢሆን ፡ ደግም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ክፉ ፡ ቢሆን ፡ ጌታችን ፡ ለለመነህ ፡ ሁሉ ፡ ስጠው ፡ ብሎ ፡ እንደተናገረ ፡ (ማቴ ፡ ፭ ፡ ፵፪) የአንዱን ፡ ሰው ፡ ተስፋ ፡ እንኳ ፡ አታሳጡ ፡ በደጋጎችና ፡ በዓመፀኞች ፡ ላይ ፡ ዝናምን ፡ እንደሚያዘንምላቸው ፡ እንደሰማያዊ ፡ አባታችሁ ፡ ፍጹማን ፡ ሁኑ ። (ማቴ ፡ ፭ ፡ ፵፰) ።

፩፻፷ ድስቅ ፡ ፲፫ ፡ የክርስቶስ ፡ ቤተ ፡ ሰብእ ፡ ባይሆኑም ፡ ለተቸገሩት ፡ ሰዎች ፡ ስጧቸው ፡ ስለዚህ ፡ ምጽዋት ፡ ሊሰጡባቸው ፡ ከሚገቡ ፡ ጊዜያቶች ፡

ያደሉ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ ፈድፋደ ፡ እምጊዜያት ፡ ፍጽምት ።

፯፻፴፩ ወለእመ ፡ ኮንት ፡ ድሉተ ፡ ለውሂብ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ ወጊዜያትሰ ፡ ፍሉጣን ፡ ዘውእቶሙ ፡ ዕለተ ፡ እሑድ ፡ ወበዓላት ፡ በእንተ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘውስተ ፡ ኦሪት ፡ በእንተ ፡ በዓላት ፡ ወኢታስተርእዩ ፡ በሙ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምላክክሙ ፡ ዕሩቃኒክሙ ፡ አላ ፡ ያውር ፡ ኵሉ ፡ ብእሲ ፡ እምኔክሙ ፡ እምዘ ፡ ጸገዎ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእምጣነ ፡ ክሂሎቱ ፡ ከመ ፡ ይባርክ ፡ ለክሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክክሙ ።

፯፻፴፪ ወበከመ ፡ ይቤ ፡ ሐዋርያ ፡ ለሰብአ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ቀዳሚት ፡ ወዘሰ ፡ ያስተጋብኡ ፡ ለቅዱሳን ፡ በከመ ፡ አዘዝክዎሙ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘገላትያ ፡ ከማሁ ፡ ግበሩ ፡ እንትሙኒ ፡ ክዕበ ፡ ኵሉ ፡ ብእሲ ፡ እምኔክሙ ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ ይፍልጥ ፡ በቤቱ ፡ በእምጣነ ፡ ተክህሎ ፡ ወይትዓቀብ ፡ ከመ ፡ ኢይኩን ፡ ቅስት ፡ እመ ፡ ምጽአትየ ፡ ኀቤክሙ ። ወባሕቱ ፡ ያአቲስ ፡ ድሉት ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ ወቃላትስ ፡ እለ ፡ ተነግሩ ፡ በእንቲአሃ ፡ ያእቲኒ ፡ በከመ ፡ ቃለ ፡ እግዚእነ ፡ ለኵሉ ፡ ዘሰአለከ ፡ ሀብ ። ወቃለ ፡ ጳውሎስኒ ፡ ዘይቤ ፡ እምጣነ ፡ ብነ ፡ ሕይወት ። ወብሂሎቶሙ ፡ ለሐዋርያት ።

፯፻፴፫ ረስጠብ ፡ ቀዳሚት ፡ ወኢታስርዉ ፡ ውሂበ ፡ እንዘ ፡ ብክሙ ፡ ዘትሁቡ ፡ እስመ ፡ ዕለተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ናሁ ፡ ቀርበ ። ወያእቲኒ ፡ ያደሉ ፡ ውሂቦታ ፡ ለእለ ፡ እቅደምን ፡ ዘክሮቶሙ ፡ ወኢመፍትው ፡ ከመ ፡ የሀቡ ፡ ለካልአን ፡ በእንተ ፡ ቃለ ፡ ሐዋርያት ።

፯፻፴፬ ድስቅ ፡ ፲ቱ ፡ ለእመ ፡ ቦ ፡ ዘይበልዕ ፡ ንዋዮ ፡ በእከይ ፡ ወበኢያእምሮ ፡ እው ፡ በስካር ፡ እው ፡ በሀኬት ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ያጽዕቅን ፡ ለመበለታተ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ወለዘከመዝ ፡ ግብሩ ፡ ኢመፍትው ፡ ይትረድእዎ ። ወበእንተዝ ፡ ይደልዎሙ ፡ ለእለ ፡ ቦሙ ፡ ተጽናስ ፡ ከመ ፡ ይንሥኡ ፡ ምጽዋተ ፡ ወይጸልዩ ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ይሁብዎሙ ፡ ወይደልዎሙ ፡ ለእለ ፡ ኢኮኑ ፡ ጽኑሳነ ፡ ከመ ፡ ኢይንሥኡ ፡ ምጽዋተ ፡ በእንተ ፡ ቃለ ፡ ሐዋርያት ። ድስቅ ፡ ፲ወ፱ቱ ፡



በእንዱ ፡ ጊዜ ፡ በምጽዋት ፡ መጠበቅ ፡ ይገባ ልና ።

፯፻፴፩ ዘወትር ፡ ለመስጠት ፡ የምትገባ ፡ ብትሆን ፡ የተለዩት ፡ ጊዜያቶች ፡ ግን ፡ እሑድና ፡ የበዓላት ፡ ቀኖች ፡ ናቸው ፡ ስለበዓላት ፡ በፈጣሪያችሁ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ባዶ ፡ እጃችሁን ፡ ሆናችሁ ፡ አትታዩ ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ በኦሪት ፡ ስለተናገረ ፡ ከእናንተ ፡ ወገን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ እንደተቻለው ፡ መጠን ፡ ይውሰድ ፡ እንጂ ፡ ፈጣሪያችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይባርካችሁ ፡ ዘንድ ። (ዘዳ ፡ ፲፮ ፡ ፲፮)

፯፻፴፪ ሐዋርያውም ፡ ለቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ በአንደኛው ፡ ክፍል ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ለምእመናን ፡ ስለሚያወጧት ፡ አስተዋጽኦ ፡ በገላትያ ፡ ያሉትን ፡ ምእመናን ፡ እንዳዘዝኋቸው ፡ እናንተም ፡ ዳግመኛ ፡ እንደዚሁ ፡ አድርጉ ። ከእናንተ ፡ ወገን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በተቻለው ፡ መጠን ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ በቤቱ ፡ ይሰጥ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ በመጣሁ ፡ ጊዜ ፡ ጠብ ፡ ክርክር ፡ እንዳይሆን ፡ ይጠበቅ ። (፩ኛ ፡ ቆሮ ፡ ፲፮ ፡ ፩-፫) ። ነገር ግን ፡ ይህችስ ፡ ዘወትር ፡ ትገባለች ፡ ስለርሷ ፡ የተነገሩ ፡ ቃላትም ፡ እኒህ ፡ ናቸው ፡ ይህችውም ፡ ጌታችን ፡ ለለመነህ ፡ ስጠው ፡ ብሎ ፡ እንደተናገረው ፡ ቃል ፡ ነው ። ጳውሎስም ፡ ሕይወታችን ፡ ሳለ ፡ እንስጥ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ሐዋርያትም ፡ የተናገሩት ፡ ይህንኑ ፡ ነው'' (ገላ ፡ ፮ ፡ ፲) ።

፯፻፴፫ ረስጠብ ፡ አንደኛ ፡ የምትሰጡት ፡ እያላችሁ ፡ መስጠትን ፡ አታቋርጡ ፡ እነሆ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ (ምጽአት) ቀርባለችና ። ይህችንም ፡ አስቀድመን ፡ ስተናገርናቸው ፡ ሰዎች ፡ መስጠት ፡ ይገባል ፡ ለሌሎች ፡ ሊሰጡቸው ፡ አይገባም ፡ ሐዋርያት ፡ ስለተናገሩ ።

፯፻፴፬ ድስቅ ፡ ፲ ፡ በስንፍና ፡ ገንዘቡን ፡ ሳያውቅ ፡ ወይም ፡ እየሰከረ ፡ ወይም ፡ በነዘህላልነት ፡ የሚመጸውት ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ስለዚህ ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ባልቴቶች ፡ ያስቸግራቸዋል ፡ ሥራው ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ ሊረዱት ፡ አይገባም ፡ ስለዚህ ፡ ችግር ፡ ያለባቸው ፡ ሰዎች ፡ ምጽዋት ፡ መቀበል ፡ ይገባቸዋል ፡ ስለሚሰጧቸውም ፡ ይጸልዩ ፡ ሐዋርያት ፡ እንደተናገሩ ፡ ያልተቸገሩ ፡ ሰዎች ፡ ምጽዋት ፡ መቀበል ፡ አይገባቸውም ። ድስቅ ፡ ፲፱ ። በእውነት ፡ ራስን ፡

ብፁዕ ፡ ዘበአማን ፡ ዘይክል ፡ ተራድኦተ ፡ ርእሱ፡ ወይሴስይ ፡ እምዘ ፡ ባሕቲቱ ፡ ወኢያጽዕቆሙ ፡ ለድክቱማን ፡ ወለፈላስያን ፡ ወለመበለታት ። እስመ ፡ እግዚእ ፡ ይቤ ፡ ብፁዕስ ፡ ፈድፋደ ፡ ዘይሁብ ፡ እምነ ፡ ዘይነሥእ ። ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ እሌሎቱ ፡ ለዘቦቱ ፡ ንዋይ ፡ ወይነሥእ ፡ ምጽዋተ ፡ ወዘኒ ፡ ይትከሀሎ ፡ ከመ ፡ ይርዳእ ፡ ነፍሶ ፡ ወይፈቱ ፡ ነሢአ ፡ እምካልኣን ፡ ወለዝንቱሰ ፡ ይትኀሠሦ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዕለተ ፡ ደይን ።

፲፻፴፭ ወዘሰ ፡ ይነሥእ ፡ በእንተ ፡ ድክትምናሁ ፡ ወእርግናሁ ፡ እው ፡ በእንተ ፡ ደዌሁ ፡ እው ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ይሴሰዩ ፡ ብዙኃን ፡ በታሕቴ ፡ እደዊሁ ፡ አልቦ ፡ ሐሜት ፡ አላ ፡ ምክሐ ፡ ይከውኖ ፡ ወያከብሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ተኈለቈ ፡ ከመ ፡ ቍርባን ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ ወይስእል ፡ ኵሎ ፡ ጊዜ ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ይሁብዎ ፡ ወኢይንሣእ ፡ ዘይነሥእ ፡ በሀኬት ፡ አላ ፡ ህየንተ ፡ ከብር ፡ እንተ ፡ ተውህበት ፡ ሎቱ ፡ ያፈድፍድ ፡ ለእለ ፡ ወሀብዎ ፡ ኪያሃ ፡ ዓስበ ፡ ጸሎት ፡ በእንተእሆሙ ፡ በአምጣነ ፡ ክሂሎቱ ። ወጳውሎስኒ ፡ ይቤ ፡ ኵሉ ፡ ዘኢይፈቅድ ፡ ይትቀነይ ፡ ኢይሴሰይ ።

፲፻፴፮ ወበእንተዝ ፡ ይደልዎ ፡ ለኵሉ ፡ ብእሲ ፡ ይትአመን ፡ ከመ ፡ ምጽዋት ፡ ታነጽሕ ፡ እምኃጢ ውእ ፡ ወትሠሪ ፡ አበሳ ፡ ወታድኅን ፡ እምኩይ ፡ ወንትዐሠይ ፡ ምክሰቢተ በእንቲአሃ ። ወዘየኀድጋኒ ፡ ለምጽዋት ፡ እንዘ ፡ ይትከሀሎ ፡ እምሳለ ፡ ከሓዲ ፡ ወእኩይ ፡ ውእቱ ፡ ወእግዚእነሂ ፡ ይቤ ፡ ሀቡ ፡ ምጽዋተ ፡ ወኵሉ ፡ ይከውን ፡ ለክሙ ፡ ንጹሐ ፡ ወሐዋርያትኒ ፡ ይቤሉ ፡ በዲድስቅልያ ፡ ፲ወ፩ቱ ።

፲፻፴፯ ወይቤ ፡ ካዕበ ፡ ዳንኤል ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ኦ ፡ ንጉሥ ፡ ያሥምርከ ፡ ምክርየ ፡ በዘይትኃደግ ፡ አበሳከ ፡ በውሂበ ፡ ምጽዋት ፡ ወዓመፃከኒ ፡ በምሒረ ፡ ነዳያን ። ወዳዊትኒ ፡ ይቤ ፡ "ብፁዕ ፡ ዘይሌቡ ፡ ላዕለ ፡ ነዳይ ፡ ወምስኪን ። እምዕለት ፡ እኪት ፡ ያድኅኖ ፡ እግዚአብሔር" ። ወሰሎሞንኒ ፡ ይቤ ፡ "ዘሰ ፡ ይፌጽም ፡ መፍቅዶ ፡ ለነዳይ ፡ ይትወሀብ ፡ ሎቱ ፡ ወይትዐሠይ ፡ ካዕበ ፡ ምክዕቢተ ፡ ወዘሰ ፡ ዐጸወ ፡ ምሕረቶ ፡ ከመ ፡ ኢይማስሉ ፡ ጽራኅ ፡ ነዳያን ፡ ውእቱኒ ፡ ካዕበ ፡

መርዳት ፡ የሚችል ፡ ሰው ፡ ብፁዕ ፡ ነው ። ካለው ገንዘቡ ፡ ብቻ ፡ የሚመገብ ፡ ደካሞቹን ፡ ስደተኞቹን ፡ ባልቴቶቹን ፡ የማያስቸግራቸውም ፡ ብፁስ ፡ ነው ። ጌታ ፡ ብፁዕስ ፡ ከሚቀበል ፡ ይልቅ ፡ የሚሰጥ ፡ ነው ፡ ብሏልና ። ዳግመኛም ፡ ገንዘብ ፡ እያለው ፡ ምጽዋት ፡ ለሚቀበል ፡ ሰው ፡ ወዮለት ፡ አለ ። ራሱን ፡ መርዳት ፡ እየተቻለው፡ ከሌሎች ፡ መቀበልን ፡ የሚወድ ፡ ሰውም ፡ ወዮለት ። እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ግን ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመረምረዋል ።

፲፻፴፭ ስለደከመ ፡ ስለ ፡ እረኛ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ታመመ፡ ወይም ፡ ከእጁ ፡ በታች ፡ የሚመገቡ ፡ ሰዎች ፡ ብዙዎች ፡ ስለሆኑ ፡ የሚመጸወት ፡ ግን ፡ ሐሜት የለበትም ። መመኪያ ፡ ይሆነዋል ፡ እግዚአብሔርም ፡ ያከብረዋል ፡ እንጂ ። ምጽዋቱ ፡ እንደ እግዚአብሔር ፡ ቍርባን ፡ ተቆጥሯልና ፡ ስለሚሰጡ ፡ ሰዎች ፡ ዘወትር ፡ ይለምን ። የሚቀበለውንም ፡ በስንፍና ፡ አይቀበል ። ስለተሰጠው ፡ ክብር ፡ ነው ፡ እንጂ ። በተቻለው ፡ መጠን ፡ ምጽዋት ፡ ለሚሰጡት ፡ ሰዎች ፡ ስለ እርሱ ፡ የጸሎቱን ፡ ዋጋ ፡ ያብዛ ። ጳውሎስም ፡ "ሊሠራ ፡ የማይወድ ፡ ሰው ፡ አይመገብ ፡ አለ" (፪ኛ ፡ ተሰ ፡ ፫ ፡ ፲) ።

፲፻፴፮ ስለዚህ ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ምጽዋት ፡ ከኃጢአት ፡ እንድታነፃ ፡ በደልን ፡ እንድታስተሠርይ ፡ ከክፋ ፡ እንደታድን ፡ ማመን ፡ ይገባዋል ። በእርሷም ፡ እጥፍ ፡ ድርብ ፡ ዋጋ ፡ እናገኛለን ። እየተቻለው ፡ ምጽዋት ፡ የማይመጸውት ፡ ሰው ፡ የከሓዲና ፡ የክፋ ፡ ግብረ ፡ አበር ፡ ነው ። ጌታችንም ፡ "ምጽዋትን ፡ ስጡ ፡ ሁሉም ፡ ለእናንተ ፡ ንጹሕ ፡ ይሆንላችኋል" ፡ አለ ። (ሉቃ ፡ ፲፩ ፡ ፵፩) ። ሐዋርያትም ፡ በዲድስቅልያ ፡ በ፲፩ኛው ፡ አንቀጽ ፡ ተናገሩ ፡ (አሉ) ።

፲፻፴፯ ዳግመኛም ፡ ዳንኤል ፡ ስለዚህ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ "ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ምክሬ ፡ ደስ ፡ ያሰኝህ ፡ ምጽዋት ፡ በመስጠትህ ፡ በደልህ ፡ ለነዳያንም ፡ በመራራትህ ፡ ዓመፃህ ፡ ይቀርልህ ፡ ዘንድ ፡" (ዳን ፡ ፬ ፡ ፳፯) ። ዳዊትም ፡ "ለድኃና ፡ ለችግረኛው ፡ የሚራራ ፡ ሰው ፡ ብፁዕ ፡ ነው ፡ ከክፉ ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ ያድነዋል ፡ አለ" ። (መዝ ፡ ፵፩ ፡ ፩) ። ሰሎሞንም ፡ "የድኃውን ፡ ፈቃድ ፡ የሚፈጽም ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ዳግመኛ ፡ እጥፍ ፡ ድርብ ፡ ዋጋ ፡ ይሰጠዋል ፡ የድሆችን ፡ ጩኸት ፡ እንዳ -

አንቀጽ ፡ ፲፯ ።

ሶበ ፡ ይስእል ፡ ኢይሰማዕ ፡ ስእለቱ ፡ ሎቱ ።

፯፻፵፰ ጌት ፡ ፳፻ ፡ ለእመቦ ፡ ዘሎቱ ፡ አዝማድ ፡ ወፈድፋደሰ ፡ ለእመ ፡ ኮኑ ፡ እምሰብአ ፡ ሃይማኖት ፡ ወኢያስተሐምም ፡ ለአሠንዮቶሙ ፡ ናሁ ፡ ክሕደ ፡ ሃይማኖቶ ፡ ወውእቱ ፡ የአኪ ፡ እምእለ ፡ ኢየአምኑ ። ወወንጌልኒ ፡ ስምዐ ፡ ይከውን ፡ "በዘይቤሎሙ ፡ እግዚእነ ፡ ለእለ ፡ ይቀውሙ ፡ በፀጋሙ ። ወአምሳሊሁ ፡ ለባዕል ፡ ዘኢወሀበ ፡ ለአልአዛር ፡ ነዳይ ፡ ወበምሳሌ ፡ ደናግል ፡ ኃምስ ፡ አብዳት ።

፯፻፵፱ ወበእንተዝ ፡ እመቦ ፡ ዘፈቀደ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ፍጹመ ፡ ይደልዎ ፡ ይመጽውት ፡ ኵሎ ፡ ንዋዮ ፡ እስመ ፡ ምጽዋትሰ ፡ በኵሉ ፡ ንዋይ ፡ ኢተአዘዘት ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ። ወቀዳሚስ ፡ በእንተ ፡ ቃለ ፡ እግዚእነ ፡ ዘይቤ ፡ እመሰ ፡ ትፈቅድ ፡ ትኩን ፡ ፍጹመ ፡ ሑር ፡ ወሢጥ ፡ ኵሎ ፡ ዘለከ ፡ ወሀብ ፡ ለነዳያን" ። ወዳግም ፡ በእንተ ፡ ቃለ ፡ ጳውሎስ ፡ ዘይቤ ፡ "ኮኑ ፡ በዝንቱ ፡ ዘመን ፡ በዘትትሜረዩ ፡ ቦቱ ፡ በግብረቲክሙ ፡ ወከመ ፡ ይኩን ፡ ተረፈ ፡ ዚአክሙ ፡ ተውሳከ ፡ ለሕጸጸ ፡ አልቦቱ ፡ ወተረፈ ፡ ዚአሆሙኒ ፡ ካዕበ ፡ ተውሳከ ፡ ለንትጋ ፡ ዚአክሙ" ። ወበእንተዝ ፡ ውሳንያቱ ፡ ሕገ ፡ ምጽዋት ፡ ኢይትገበር ፡ በአድልዎ ፡ ወከመ ፡ ይትወሀብ ፡ በፍሥሐ ፡ ዘእንበለ ፡ ኀዘን ፡ ወከመ ፡ ኢይንስሑ ፡ በእንቲአሃ ።

፯፻፶ ወይኩን ፡ ወሃቢሃ ፡ መፍቀሬ ፡ ሰብእ ፡ ዘኢኮነ ፡ ተዓባዪ ፡ ላዕለ ፡ ዘይሁቦ ፡ ምጽዋተ ፡ ወከመ ፡ ኢይትሐሰቦ ፡ በእንቲአሃ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ወኢይትኃሠሥ ፡ በእንተ ፡ መግቦቱ ፡ ኪያሃ ። ወኢይናፍቅ ፡ እላ ፡ ያእምር ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፈድዮ ፡ በእንቲአሃ ።

፯፻፶፩ ወትኩን ፡ ንዋይ ፡ ዘአልቦ ፡ ነውር ፡ ወዝንቱኒ ፡ ከመ ፡ ቃለ ፡ እግዚእነ ፡ ዘይቤ ፡ "ኢትግበሩ ፡ ምጽዋተክሙ ፡ በቅድመ ፡ ሰብእ ፡ ከመ ፡ ይርአዩክሙ ፡ ወእመ ፡ አኮሰ ፡ ዓስብ ፡ አልብክሙ ፡ በኀበ ፡ አቡክሙ ፡ ሰማያዊ ። ወለእመ ፡ ገበርክሙ ፡ ምጽዋተ ፡ ኢትንፋኁ ፡ ቀርነ ፡ ከመ ፡ ይገብሩ ፡ መደልዋን ፡ በጉባኤ ፡ ወበፍናዋት ፡ ከመ ፡ ይትአኰቱ ፡ እምሰብእ ፡ አማን ፡ እብለክሙ ፡ ነሥኡ ፡ ዕሴቶሙ" ።

ስለ ፡ ምጽዋት ።

ይሰማ ፡ ቸርነቱን ፡ የዚያ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ እሱም ፡ ዳግመኛ ፡ በለመነ ፡ ጊዜ ፡ ልመናው ፡ አይሰማለትም ፡" አለ ። (ምሳ ፡ ፳፩ ፡ ፲፫-፲፬) ።

፯፻፵፰ ጢት ፡ ፳ ፡ ዘመዶች ፡ ያሉት ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ይልቁንም ፡ ከሃይማኖት ፡ ሰዎች ፡ ወገን ፡ ቢሆኑ ፡ እነርሱን ፡ ለመርዳት ፡ ባያስብ ፡ እነሆ ፡ ሃይማኖቱን ፡ ካደ ፡ ከማያምኑም ፡ ሰዎች ፡ እርሱ ፡ ይከፋል ። (፩ኛ ፡ ጢሞ ፡ ፭ ፡ ፰) ። ወንጌልም ፡ በግራ ለሚቆሙ ፡ ሰዎች ፡ ጌታ ፡ ያለውን ፡ ይመሰክራል ፡ ለተቸገረው ፡ አልአዛር ፡ ባልሰጠው ፡ ባለጸጋና ፡ በአምስቱ ፡ ሰነፎች ፡ ደናግል ፡ ይመስላል ።

፯፻፵፱ ስለዚህ ፡ ፍጹም ፡ ሊሆን ፡ የወደደ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ መመጽወት ፡ ይገባዋል ። ገንዘብን ፡ ሁሉ ፡ መመጽወት ፡ ግን ፡ ለሰው ፡ ሁሉ፡ አልታዘዘችምና ። መጀመሪያውስ ፡ "ፍጹም ፡ ልትሆን ፡ ከወደድክስ ፡ ሂደህ ፡ ያለህን ፡ ገንዘብህን ፡ ሁሉ ፡ ሸጠህ ፡ ለነዳያን ፡ ስጥ ፡ ብሎ ፡ ጌታችን ፡ እንደተናገረ ፡ ነው ።" (ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፳፩) ። ሁለተኛም ፡ ጳውሎስ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ በሥራችሁ ፡ ተካከላችሁ ፡ ኑሩ ፡ ብሎ ፡ ስለተናገረ፡ ነው ። የእናንተ ፡ ተረፍ ፡ የእነዚያን ፡ ጕድሎ ፡ ይሞላው ፡ ዘንድ ፡ ዳግመኛም ፡ የእነሱ ፡ ተረፍ ፡ የእናንተን ፡ ጕድሎ ፡ ይሞላው ፡ ዘንድ ። (፪ኛ ፡ ቆሮ ፡ ፰ ፡ ፲፬) ። ስለዚህ ፡ የምጽዋት ፡ ሕግ ፡ ውሳኔ ፡ በማድላት ፡ አይሠራ ። ያለ ፡ ኀዘን ፡ በደስታ ፡ እንዲሰጥ ፡ ስለርሷም ፡ እንዳይጸጸቱ ።

፯፻፶ ሰጭዋም ፡ ምጽዋቱን ፡ በሚሰጠው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የሚታበይ ፡ የይደለ ፡ ሰው ፡ ወዳጅ ፡ ይሁን ። ስለእርሷም ፡ ኤጲስቆጶሱን ፡ እንዳይቆጣጠረው ፡ እርሷን ፡ በማስተዳደሩ ፡ እንዳይመራመረው ፡ አይጠራጠር ፡ በእርሷ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲከፍለው ፡ ይወቅ ፡ እንጂ ።

፯፻፶፩ ምጽዋት ፡ ነውር ፡ የሌለባት ፡ ትሁን ፡ ያዩላችሁ ፡ ዘንድ ፡ ምጽዋታችሁን ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ አታድርጉ ፡ ብሎ ፡ ጌታችን ፡ እንደተናገረ ። ይህ ፡ ካልሆነ ፡ ግን ፡ በሰማያዊ ፡ አባታችሁ ፡ ዘንድ ፡ ዋጋ ፡ የላችሁም ። ምጽዋት ፡ ብታደርግ፡ ነጋሪት ፡ አትምታ ፡ ግብዞች ፡ በአደባባይና ፡ በመንገድ ፡ እንደሚያደርጉት ፡ ከሰው ፡ ይመሰገኑ ፡ ዘንድ ፡ በእውነት ፡ ዋጋቸውን ፡ አገኙ ። (ማቴ ፡ ፮ ፡ ፩ - ፪) ።

፮፻፵፱ ትሃ ፡ ወኢትኅዝን ፡ ሶበ ፡ መጽወትከ ፡ ለአኁከ ። ወበከመ ፡ ይቤ ፡ ሐዋርያ ፡ "ኵሉ ፡ ብእሲ ፡ እምኔክሙ ፡ በከመ ፡ ሐለየ ፡ በልቡ ፡ ይግበር ፡ ወአኮ ፡ ከመ ፡ ዘይከውን ፡ በትዕግልት ፡ ወበኀዘን ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያፈቅሮ ፡ ለወሃቢ ፡ ዘይሁብ ፡ በፍሥሓ" ። ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ እመ ፡ አብላዕኩ ፡ ኵሎ ፡ ዘብየ ፡ ለነዳያን ፡ ወአልብየ ፡ ተፋቅሮ ፡ እልቦ ፡ ዘረባሕኩ ።

፮፻፶ ጌጥ ፡ ወኢትስድዶ ፡ ለምስኪን ፡ እምአንቀጸ ፡ ቤትከ ፡ ወኢትትዐወሮ ፡ እምቃሉ ፡ ወኢትገሥጾ ፡ ወኢታስተሐቅሮ ። አላ ፡ አክብሮ ፡ እምሕሊናከ ፡ ከመ ፡ ትናዝዞ ፡ ወታስተፍሥሖ ፡ ለከ ፡ ከመ ፡ ያስተፍሥሕከ ፡ እግዚአብሔር ። ወእንብሮ ፡ ምስሌከ ፡ ጊዜ ፡ ማእድከ ፡ ወበዐዋዕ ፡ ዘትሰቲ ፡ ቦቱ ፡ አስትዮ ፡ ወኢትትመካሕ ፡ ላዕሌሁ ።

፮፻፶፩ ድስቅ ፡ ፯ቱ ፡ ወኢያደሉ ፡ ከመ ፡ ትትሐሰቦ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ወኢትሕትት ፡ በእንተ ፡ ምግባሩ ፡ ዘከመ ፡ እፎ ፡ ይገብር ፡ አው ፡ በእይ ፡ ዘመን ፡ ወበአይ ፡ መካን ፡ አው ፡ ለዘወሀበ ፡ አው ፡ ቦኑ ፡ ያሤኒ ፡ ምግባሩ ፡ በከመ ፡ ይደሉ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወሀቦ ፡ ሎቱ ፡ ዘንተ ፡ ምግብና ።

፮፻፶፪ ረስጠብ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ወለእመ ፡ ብከ ፡ ምንትኒ ፡ እምንዋይት ፡ ወወሀብከ ፡ እምኔሁ ፡ እንዘ ፡ ተነሥሥ ፡ መድኃኒተ ፡ ነፍስከ ፡ እምእበሳከ ፡ ኢትኩን ፡ ዘ፪ኤ ፡ ልቡ ፡ ወለእመ ፡ ወሀብከ ፡ ንዋየከ ፡ አእምር ፡ መኑ ፡ ውእቱ ፡ ዘይፈድየከ ።

፮፻፶፫ ወሐዋርያትኒ ፡ አዘዙ ፡ ከመ ፡ ኢይንሥኡ ፡ ምጽዋተ ፡ እምእደ ፡ እኩያን ፡ ዘተዘከሩ ፡ በአንቀጸ ፡ ቍርባን ፡ ወይቤሉ ። ድስቅ ፡ ፳ወ፩ዱ ፡ ወለእመ ፡ ትብሉ ፡ እስመ ፡ እሉ ፡ እለ ፡ ይሁቡ ፡ ምጽዋተ ፡ ለእመ ፡ ኢነሣእነ ፡ እምኔሆሙ ፡ ምንተኑ ፡ ንሴስዮሙ ፡ ለመበለታት ፡ ወበምንት ፡ ናልዘቆሙ ፡ ለደካትም ፡ ወንሁቦሙ ፡ ለጽኑሳን ፡ ዘውስተ ፡ ሕዝብ ፡ ይስምዑ ፡ እምኔነ ፡ እለ ፡ ከመዝ ፡ ይብሉ ። አኮኑ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ትነሥኡ ፡ ክብረ ፡ ሌዋውያን ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ቀዳምያተ ፡ እክል ፡ ወነሢእ ፡ በኵር ፡ ዘይሁቡ ክሙ ፡ ሕዝብክሙ ፡ ዘየአክለክሙ ፡ ለርእስክሙ ፡ ወዘየአክሎሙ ፡ ለጽኑሳን ፡ ወኢትፍቅዱ ፡ ከመ ፡ ትንሥኡ ፡ እምእኩያን ። ወለእመ፡



፮፻፵፱ ትሃ ፡ ለወንድምህ ፡ በመጸወትኸው ፡ ጊዜ ፡ አትዘን ። ሐዋርያው ፡ እንዳለ ፡ ከእናንተ ፡ ወገን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በልቡ ፡ ያሰበውን ፡ ያድርግ ፡ በቅሚያ ፡ በማኅዘን ፡ የሚሆን ፡ አይደለም ። በደስታ የሚሰጠውን ፡ ሰጭ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይወደዋልና ። (፪ኛ ፡ ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፯) ። ዳግመኛም ፡ ያለኝን ፡ ሁሉ ፡ ለነዳያን ፡ ባበላ ፡ ፍቅር ፡ ከሌለኝ ፡ የተጠቀምሁት ፡ የለም ፡ አለ ። (፩ኛ ፡ ቆሮ ፡ ፲፫ ፡ ፫) ።

፮፻፶ ጌጥ ፡ ድኃውን ፡ ከቤትህ ፡ ደጃፍ ፡ አታሳድደው ከንግግሩ ፡ የተነሳ ፡ ቸል ፡ አትበለው ፡ አትቆጣው ፡ አታቃለው ። ታረጋጋው ፡ ደስ ፡ ታሰኘው ፡ ዘንድ፡ አንተንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ደስ ፡ ያሰኝዘ ፡ ዘንድ ፡ ከልብህ ፡ አክብረው ፡ እንጂ ። በማዕድህ ፡ ጊዜ ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ አስቀምጠው ፡ በምትጠጣበትም ፡ ጽዋ ፡ አጠጣው ፡ አትመካበትም ።

፮፻፶፩ ድስቅ ፡ ፯ ፡ ኤጲስቆጶሱን ፡ ልትቆጣጠረው ፡ አይገባም ። እንደምን ፡ ይሠራዋል ፡ ብለህ ፡ ስለ ፡ ሹመቱ ፡ አትመራመር ፡ በመቸ ፡ ዘመን ፡ በዬት ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ ለማን ፡ ሰጠው ፡ ወይም፡ እንደሚገባው ፡ በሹመቱ ፡ ያስተዳድርበታል ? ብለህ ። ይህን ፡ ሹመት ፡ እግዚአብሔር ፡ ለርሱ ፡ ሰጥቶታልና ።

፮፻፶፪ ረስጠብ ፡ ፲፪ ፡ ከገንዘብ ፡ ወገን ፡ ምንም ፡ ቢኖርህ ፡ ከበደልህ ፡ የተነሳ ፡ የነፍስህን ፡ ድኅነት ፡ ስትሻ ፡ ከርሱ ፡ ብትሰጥ ፡ ሁለት ፡ ልብ ፡ አትሁን ። ገንዘብህን ፡ ብትሰጥ ፡ የሚከፍልህ ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ እወቅ ።

፮፻፶፫ ሐዋርያትም ፡ በአንቀጸ ፡ ቍርባን ፡ ከተነገሩት፡ ከክፉዎች ፡ እጅ ፡ ምጽዋትን ፡ አይቀበሉ ፡ ብለው ፡ አዘዙ ። (ፍ ፡ ነገ ፡ ፲፫ ፡ ፭፻፩ ።) ድስቅ ፳፩ ፡ ምጽዋት ፡ የሚሰጡ ፡ እሊህ ፡ ናቸው ፡ እኮ ፡ ብትሉ ፡ ከነርሱ ፡ ካልተቀበልን ፡ ባልቴቶችን ፡ ምን ፡ እንመግባቸዋለን ? ድኃ ፡ አደጎችን፡ በምን ፡ እናሳድጋቸዋለን ? ከሕዝቡ ፡ ወገን ፡ ለተቸገሩት ፡ ምን ፡ እንሰጣቸዋለን ? ብትሉ ፡ እንዲህ ፡ የሚሉ ፡ ከእኛ ፡ ይስሙ ። ስለዚህ ፡ የሌዋውያንን ፡ ሀብት ፡ የምትቀበሉ ፡ አይደላችሁምን ? ይህችውም ፡ የእህሉ ፡ መጀመሪያ ፡ ናት ፡ ለራሳችሁ ፡ የሚበቃችሁን ፡ ለተቸገሩትም ፡ የሚበቃቸውን ፡ ወገኖቻችሁ ፡ የሚሰጡችሁ ፡ በኵራት ፡ ነው ። ከክፉዎችም ፡ መቀበ

ኮነት ፡ ጉባዔ ፡ ዘለንታሃ ፡ ትገብር ፡ ከመዝ ፡ ወአልቦ ፡ ሠናያት ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ስብእ ፡ ባቲ፡ ይሄይስክሙ ፡ ትሙቱ ፡ ወትማስኑ ፡ በረኃብ ፡ ፈድፋደ ፡ እምትንሥኡ ፡ እምአፅራረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወውእቱ ፡ ይከውን ፡ ስሐቀ ፡ ወስላቀ ፡ ማእከለ ፡ አብያጺሁ ፡ ወበእንተ ፡ እሉ ፡ ይቤ ፡ ነቢይ ፡ ቅብአ ፡ ኃጥአንስ ፡ ኢይትቀባእ ፡ ርእ ስየ ።

፯፻፵፯ ድስቅ ፡ ፳ወ፩ዱ ፡ ወኩኑ ፡ አመካርያነ ፡ ለኵሉ ፡ ስለ፩ዱ ፡ እምኔክሙ ፡ ወተወከፍዎ ፡ ለዘየሐ ውር ፡ ሑረተ ፡ ርቱዐ ፡ በኵሉ ፡ ግብር ፡ ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ በእንተ ፡ ዓጸባ ፡ ትነ ሥኡ ፡ ብፉረ ፡ እምዘ ፡ ኢትፈትዉ ፡ ዘውእቱ ፡ እምብእሲ ፡ ርኩስ ፡ ዘኢየአምን ፡ ረስይዎ ፡ ለሤጠ ፡ ዕፀው ፡ ወለአንድዶ ፡ ከመ ፡ ኢይን ሥኡ ፡ እምኔሁ ፡ መበለታት ፡ ወእጓለ ፡ ማውታ ወኢይጽሀቁ ፡ ከመ ፡ ይሣየጡ ፡ ቦቱ ፡ መብልዐ፡ ወመስቴ ፡ በዘኢይደሉ ፡ ርቱዕ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ መብልዐ ፡ ለእሳት ፡ ዝንቱ ፡ ንዋየ ፡ ዐማዕያን ፡ ወኢይኩን ፡ መብልዐ ፡ ለቅዱሳን ።

፯፻፵፰ ክፍል ፡ ይደልዎ ፡ ለዘያስተጋብእ ፡ ሎቱ ፡ ንዋየ ፡ ዘቦቱ ፡ ዕቅፍት ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ገብረ፡ ዓመፃ ፡ በአስተጋብእተ ፡ ዚእሁ ፡ ኢያስተጋ ብእ ፡ እንከ ፡ ምስለ ፡ ዝንቱ ፡ ኀጢአ ፡ ጽድቅ ፡ ሒ ኀክር ፡ በእንተ ፡ ምጽዋት ፡ በሐልዮቱ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ዘኢይደመስስ ፡ አበሳሁ ። አላ ፡ ይትነሳሕ ፡ እምዝንቱ ፡ ምግባር ፡ ወይሚጥ ፡ ንዋየ ፡ ለዘነሥእ ፡ በትዕግልት ። ወለእመስ ፡ ኢተክህሎ ፡ ይክፍል ፡ ወየሀቦሙ ፡ ለነዳያን ፡ በከመ ፡ አዘዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ በኦሪት ፡ ወበወ ንጌል ።

፯፻፵፱ ወኦሪትሰ ፡ በእንተ ፡ ትእዛዙ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ በውስቴታ ፡ ከመ ፡ ያግብኡ ፡ ተዓጋል ያን ፡ በጊዜሁ ፡ ንዋየ ፡ ዘተዓገሉ ፡ ወ፩ተ ፡ እደ ፡ በአምሳሊሁ ፡ ለዘሄድዎ ፡ ወያቅርቡ ፡ ቍርባነ ፡ ለእግዚአብሔር ። ወሶበ ፡ ኢተረከበ ፡ ውእቱ ፡ ወኢ፩ዱ ፡ እምአዝማዲሁ ፡ ይረስይዎ ፡ ለእግዚ አብሔር ፡ ወየሀብዎ ፡ ለካህን ፡ ምስለ ፡ ቍር ባን ።

፯፻፶ ወወንጌልኒ ፡ በእንተ ፡ ዘይቤ ፡ እግዚእነ ፡ በም ሳሌ ፡ ለዘሰመዮ ፡ መጋቤ ፡ ዓመፃ ፡ ዘጸውዖሙ ፡ ለእለ ፡ ይፈድይዎ ፡ ዕዳ ፡ ለእግዚኡ ፡ ውኅደ ፡

በልን ፡ አትውደዱ ። ሁለመናዋ ፡ የተሰበሰበ ችው ፡ ኃጢአተኛ ፡ ብትሆን ፡ እንደዚህ ፡ ብታደ ርግ ፡ ሰው ፡ ይኖርባት ፡ ዘንድ ፡ ደግ ፡ ነገር ፡ ባይኖር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጠላቶች ፡ ምጽዋት ፡ ከምትቀበሉ ፡ ፈጽማችሁ ፡ በረኃብ ፡ ብትሞቱ ፡ ይሻላችኋል ። ይኸውም ፡ በባልንጀሮቹ ፡ መካ ከል ፡ መሳለቂያ ፡ መዘባበቻ ፡ ይሆናል ። ስለእ ነርሱም ፡ ነቢይ ፡ "የኃጥአንን ፡ ቅባት ፡ ራሴ ፡ አይቀባም ፡ አለ" (መዝ ፡ ፻፵፩ ፡ ፭) ።

፯፻፵፯ ድስቅ ፡ ፳፩ ፡ ከእናንተ ፡ ወገን ፡ ሁሉን ፡ ለአያን ዳንዱ ፡ የምትፈትኑ ፡ ሁኑ ። በሥራው ፡ ሁሉ ፡ በቀና ፡ ሥራ ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖረውን ፡ ተቀበሉት። ዳግመኛም ፡ አለ ፡ ከማትወዱት ፡ ይኸውም ፡ ከማያምን ፡ ከኃጢአተኛ ፡ ሰው ፡ ስለችግር ፡ የምትቀበሉ ፡ ከሆነ ፡ እንጨት ፡ ገዝታችሁ ፡ አን ድዱበት ። ባልቴቶቹ ፡ እናት ፡ አባት ፡ የሞተባ ቸው ፡ ከእርሱ ፡ እንዳይወስዱ ፡ በማይገባው ፡ ገንዘብ ፡ መብል ፡ መጠጥ ፡ ይገዙበት ፡ ዘንድ ፡ እንዳይተጉ ። ይህ ፡ የኃጢአተኞች ፡ ገንዘብ ፡ በእሳት ፡ ሊቃጠል ፡ ይገባል ፡ የምእመናን ፡ (የቅዱሳን) ምግብ ፡ አይሁን ።

፯፻፵፰ ክፍል ፡ መሰናክል ፡ ያለበትን ፡ ገንዘብ ፡ የሚሰ ብስብ ፡ ሰው ፡ ገንዘብ ፡ በመሰብሰቡ ፡ ኃጢአት ፡ አድርጓልና ፡ እንዳይሰበስብ ፡ ይገባዋል ። ከዚ ህም ፡ ጋር ፡ ስለምጽዋቱ ፡ በደሉ ፡ እንደማይሠ ረይለት ፡ በማሰቡ ፡ የእውነትንና ፡ የምክርን ፡ ማጣት ፡ እንግዲህ ፡ አይሰብስብ ። ከዚህ ፡ ሥራው ፡ ይመለስ ፡ እንጂ ፡ በጉልበት ፡ የቀማ ውንም ፡ ገንዘብ ፡ ይመልስ ። መመለስ ፡ ባይቻ ለው ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ በኦሪትና ፡ በወን ጌል ፡ እንዳዘዘ ፡ ለነዳያን ፡ ከፍሎ ፡ ይስጣቸው ።

፯፻፵፱ በኦሪትስ ፡ ገንዘብ ፡ የቀሙ ፡ ሰዎች ፡ ወዲያው ፡ ለቀሙት ፡ ሰው ፡ በመሰሉ ፡ ፭ ፡ እጅ ፡ ጨም ረው ፡ ይመልሱ ፡ ዘንድ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ስለአዘዘ ፡ ነው ። ለእግዚአብሔርም ፡ ቍርባን ፡ ያቅርቡ ። እርሱ ፡ ከዘመዶቹም ፡ አንዱ ፡ ባይ ገኝ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ገንዘብ ፡ አድርገው ፡ ከመጣው ፡ ጋር ፡ ለካህኑ ፡ ይስጡት ። (ዘፀ ፡ ፳፪ ፡ ፩ - ፬) ።

፯፻፶ በወንጌልም ፡ ጌታችን ፡ ለጌታው ፡ ዕዳ ፡ የሚከ ፍሉትን ፡ ሰዎች ፡ ጠርቶ ፡ የጌታውን ፡ ገንዘብ ፡ እኩሌታውን ፡ ለተወላቸው ፡ ዐመፀኛ ፡ ሹም ፡

ሎሙ ፡ መንፈቀ ፡ ንዋዮ ፡ ዘእግዚኡ ፡ ወይቤ ፡ ወንጌላዊ ፡ ወንእዶ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለመጋቤ ፡ ዓመፃ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ጠቢብ ፡ ገብረ ። ወይቤ ፡ እግዚእነ ፡ ወእንሂ ፡ እብለክሙ ፡ ግበሩ፡ ለክሙ ፡ እዕርክተ ፡ እምንዋየ ፡ ዓመፃ ፡ ከመ ፡ ሶበ ፡ አኅለቅሙ ፡ ይትወከፉክሙ ፡ ውስተ ፡ አብያቲሆሙ ፡ ዘለዓለም ። ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ እመሰ ፡ ኢተረከብክሙ ፡ ምእመናነ ፡ በንዋየ ፡ ዓመፃ ፡ መኑ ፡ ይትእመነክሙ ፡ በንዋየ ፡ ጽድቅ ። ወሶበ ፡ በንዋየ ፡ ባዕድ ፡ ኢተረከብክሙ ፡ ምእመናነ ፡ መኑ ፡ ይሁብክሙ ፡ ንዋየክሙ ።

፮፻፶፩ ወወደሳ ፡ እግዚእነ ፡ ለዘማዊት ፡ ዘወሀበት ፡ ንዋያ ፡ ለመልእክተ ፡ ዚአሁ ፡ እመ ፡ ነስሐት ፡ እም፡ነግውእ ፡ ወኢያስተኀፈሮ ፡ እግዚእ ፡ እምተሰፋ ፡ ድኂን ፡ ለዘኬዎስ ፡ ሶበ ፡ ይቤሎ ፡ እመሂ ፡ ቦ ፡ ዘገፋዕክዎ ፡ እፈድዮ ፡ ህየንተ ፡ ፩ዱ ፡ ትርብዕተ ፡ ወእሁብ ፡ መንፈቀ ፡ ንዋይየ ፡ ለነዳያን ።

፮፻፶፪ ወበከመ ፡ ይነግር ፡ መጽሐፈ ፡ አብረክሲስ ፡ ሀከመ ፡ ኮኑ ፡ ሐዋርያት ፡ ይነሥኡ ፡ ንዋየ ፡ እምእመናን ፡ ወይሁብዎ ፡ ለለ፩ዱ ፡ ፩ዱ ፡ ብእሲ ፡ በበመፍቅዱ ። ወዕውቅ ፡ ውእቱ ፡ ከመ፡ እሉ ፡ ምስለ ፡ ብዝኆሙ ፡ ወበእንተ ፡ ዘኢኮኑ ፡ ምእመናነ ፡ ኢይትኀደግ ፡ ግብር ፡ ከመ ፡ ይኩን፡ እመቦ ፡ እምውስቴቶሙ ፡ ዘቦ ፡ ነውር ፡ ውስተ፡ ንዋዩ ። ወምስለ ፡ ዝንቱ ፡ ናሁ ፡ እርድእት ፡ ይትዌከፉ ፡ ንዋዮሙ ፡ በጊዜ ፡ ግብእቶሙ ፡ ወእሚኖቶሙ ፡ ወይሁብዎሙ ፡ ለጽኑሳን ፡ እምኔሁ ። ወናሁ ፡ ይቤ ፡ ቅዱስ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ታኦጎሎስ ፡ በዮንቱ ፡ ድርሳኑ ፡ እንተ ፡ ተናገረ ፡ ባቲ እምድኅረ ፡ አርምሞቱ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ሀኢኮነ ግብር ፡ እምዘይትቀረብ ፡ ንኡስ ፡ ውእቱ ፡ ወለእመኒ ፡ ውስተ ፡ ዘይንእስ ፡ እምግብራት ፡ አርኃቃ ፡ እምትእዛዙ ፡ ርቱዕ ፡ ኢይትኀደግ ፡ ግብር ፡ ዘቀደመ ፡ ወሀእቅረብዎስ ፡ እምሁለሄ ፡ ኢይትወከፉ ።



በተሰኘው ፡ መስሎ ፡ ስለተናገረ ፡ ነው ። ወንጌላዊውም ፡ በመፀኛውን ፡ ሹም ፡ እግዚአብሔር ፡ አመሰገነው ፡ አለ ፡ የእዋቂ ፡ ሥራ ፡ ሠራ። ጌታችንም ፡ አለ ፡ "እኔም ፡ በኀላፊው ፡ ገንዘብ ፡ ወዳጆች ፡ አውጡበት ፡ እላችኋለሁ ። በጨረሳችሁም ፡ ጊዜ ፡ በዘለዓለም ፡ቤታቸው ፡ ይቀበሏችሁ ፡ ዘንድ ፡ ዳግመኛም ፡ በሚያልፈው ፡ ገንዘብ ፡ የምትታመኑ ፡ ሁናችሁ ፡ ካልተገኛችሁ ፡ በማያልፈው ፡ ገንዘብ ፡ ማን ፡ ያምናችኋል ? በባዕድም ፡ ገንዘብ ፡ የምትታመኑ ፡ ሁናችሁ ፡ ካልተገኛችሁ ፡ ገንዘባችሁን ፡ ማን ፡ ይሰጣችኋል ?" (ሉቃ ፡ ፲፮ ፡ ፩-፲፪) ።

፮፻፶፩ ጌታችንም ፡ ከኃጢአቷ ፡ በተመለሰች ፡ ጊዜ ፡ እርሱን ፡ ለማገልገል ፡ ገንዘቧን ፡ የሰጠች ፡ ዘማዊትን ፡ አመሰግናት ። (ሉቃ ፡ ፯ ፡ ፴፮-፵፰) ። የበደልኩት ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ በእንድ ፡ አራት ፡ እከፍለዋለሁ ፡ የገንዘቤንም ፡ እኩሌታ ፡ ለነዳያን ፡ እሰጣለሁ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ጌታ ፡ ዘኬዎስን ፡ እድናለሁ ፡ ከማለት ፡ ተስፋ ፡ እላሳፈረውም ። (ሉቃ ፡ ፲፱ ፡ ፪ - ፰) ።

፮፻፶፪ ሐዋርያት ፡ ከምእመናን ፡ ወገን ፡ ገንዘብ ፡ ይቀበሉ ፡ እንደነበር ፡ የሐዋርያት ፡ ሥራ ፡ (መጽሐፍ) ፡ እንደሚናገረው ፡ ለእያንዳንዱም ፡ ሰው፡ በየፈቃዱ ፡ ይሰጡት ፡ ነበር ። እሊህ ፡ ከብዙዎቹ ፡ ጋር ፡ ምእመናንን ፡ ስላልሆኑ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ሥራው ፡ እንዳማይቀር ፡ የታወቀ ፡ ነው ፡ ከእነርሱም ፡ ወገን ፡ በገንዘቡ ፡ ነውር ፡ ያለበት ፡ ሲሆን ። ከዚህም ፡ ጋር ፡ እነሆ ፡ ሐዋርያት ፡ በተመለሱ ፡ ባመኑ ፡ ጊዜ ፡ ገንዘባቸውን ፡ ይቀበሉ ፡ ነበር ፡ ከገንዘቡም ፡ ለተቸገሩት ፡ ይሰጧቸው ፡ ነበር ። (የሐዋ ፡ ፪ ፡ ፵፬ - ፵፮) ። እነሆ ፡ ነባቢ ፡ መለኮት ፡ ቅዱስ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ከሕርመቱ ፡ በኋላ ፡ በተናገረው ፡ በድርሰቱ ፡ መጀመሪያ ፡ ከሚመጸወተው ፡ ገንዘብ ፡ ወገን ፡ የማይገባ ፡ ገንዘብ ፡ ቢሆን ፡ ትንሽም ፡ ቢሆን ፡ ከሥራም ፡ ወገን ፡ እነስተኛ ፡ ቢሆን ፡ ከቀናው ፡ ሕጉም ፡ ቢያርቃት ፡ በቀደመው ፡ ሥራ ፡ ሲቀር፡ እይገባውም ። ሳይመለሱ ፡ ከሁሉም ፡ ወገን ፡ ያቀረቡትን ፡ ግን ፡ እይቀበሉ ።

## አንቀጽ ፡ ፲ወ፯ቱ ።

በእንተ ፡ ዘይሠየም ፡ ላዕለ ፡ ንዋየ ፡ ምጽዋት ፡ ወንዋየ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወቍርባናቲሃ ፡ ወዘከመ ፡ ይደሉ ፡ ውሂቦታ ፡ ወከፊሎታ ፡ ወኵሉ ፡ ዘይከውን ፡ ባቲ ።

፮፻፶፫ ወውእቱ ፡ ኀበ ፡ ፫ቱ ፡ እክፋል ። ቀዳሚ ፡ ከመ ፡ የእዝዝ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በኵሉ ፡ ንዋየ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወያስተዋዕእ ፡ እምኔሁ ፡ ዘይፈቅድ ለሊሁ ፡ ለርእሱ ፡ ወለጽኑሳን ፡ እምቀሳውስት ፡ ወዲያቆናት ።

፮፻፶፬ ረስጠጅ ፡ ፵ ፡ ንእዝዝ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሥሉጠ ፡ ላዕለ ፡ ንዋየ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ። እምከመሰ ፡ ኮነ ፡ ዘተአመንዎ ፡ ላዕለ ፡ ነፍሳተ ፡ ሰብእ ፡ ክቡራት ፡ ምንትኑ ፡ ይእቲ ፡ ኵላ ፡ ንዋይ ፡ ወጥሪት ፡ ዘይሁብዎ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይመግብ ፡ በትእዛዙ ፡ ዘይሴስዮሙ ፡ ለነዳያን ፡ እምኔሃ ፡ በእደዊሆሙ ፡ ለቀሳውስት ፡ ወዲያቆናት ፡ በፍርሃተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወበረዓድ ፡ ወካዕበ ፡ ይንሥእ ፡ እምኔሃ ፡ ወየሃብዎሙ ፡ መፍቅዶሙ ፡ ለፈቃድያን ፡ አኃው ፡ ወለእናግድ ፡ እለ ፡ ይሔውጽዎ ።

፮፻፶፭ ዘሉቃስ ፡ "ወሐዋርያትኒ ፡ ኮኑ ፡ ይሁብዎሙ ፡ ለሰብእ ፡ ለለ፩ዱ ፡ ፩ዱ ፡ በከመ ፡ መፍቅዱ ፡ እምዘ ፡ ኮኑ ፡ ያመጽኡ ፡ ኀቤሆሙ ።

፮፻፶፮ ረስጣ ፡ ጽወ፳ቱ ፡ ወለየሐሊ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ኵሎ ፡ ዘሀሎ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወይሥራዕ ፡ ዘከመ ፡ ይሬእዮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሀሎ ፡ ወኢይደሉ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይንሣእ ፡ ረባሐ ፡ እምኔሃ ፡ ለባሕቲቱ ፡ ለነጊድ ፡ ወኢከመ ፡ የሀብ ፡ ንዋየ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእዝማዲሁ ፡ ወእመኒ ፡ ኮኑ ፡ ነዳያን ፡ ወኢከመ ፡ ይንግድ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በምክንያቶሙ ፡ ለሰብእ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘይፈቅዱ ።

፮፻፶፯ ጾክ ፡ ጽወ፰ቱ ፡ ወለእመሰ ፡ ኢኀደገ ፡ ዘንተ ፡ ወአስተዋጽአ ፡ ለሲሳየ ፡ ዚአሁ ፡ ሎቱ ፡ ወለአስተዋጽአተ ፡ ሰብእ ፡ ቤቱ ፡ ወኢያርአዮሙ ፡ ለቀሳውስት ፡ ወለዲያቆናት ፡ ንዋየ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይኩን ፡ ውፁእ ፡ ምስለ ፡ ሰብአ ፡ ቤቱ ፡ ወባሕቱ ፡ ኢይፃእ ፡ ቀሲስ ፡ አው ፡ ዲያቆን ፡ ወኢይርኀቅ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከመ ፡ ኢይትሐዘብዎ ፡ ጉባኤ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ።



## አንቀጽ ፡ ፲፯ ።

በምጽዋት ፡ ገንዘብ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገንዘብ ፡ በመባዋ ፡ ላይ ፡ ስለሚሾም ፡ ሹምና ፡ ከፍሎ ፡ መስጠት ፡ ስለሚገባው ፡ በእርሷም ፡ ስለሚሆነው ፡ ሁሉ ።

፮፻፶፫ ይኸውም ፡ ከ፫ ፡ ይከፈላል ። መጀመሪያ ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ ያዝዝ ፡ ዘንድ ፡ ከርሱ ፡ ለራሱ ፡ ከቀሳውስትና ፡ ከዲያቆናትም ፡ ወገን ፡ ለተቸገሩት ፡ የሚሻውን ፡ ያወጣጣ ፡ ዘንድ ።

፮፻፶፬ ረስጠጅ ፡ ፵ ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ የሥለጠነ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ እናዝዛለን ። በከበሩት ፡ ሰዎች ፡ ነፍሳት ፡ ላይ ፡ የሚያምኑት ፡ ከሆነ ፡ በትእዛዙ ፡ ያስተዳድርባት ፡ ዘንድ ፡ የሚሰጡት ፡ ገንዘብና ፡ ጥሪት ፡ ሁሉ ፡ ምንድን ፡ ናት ። እግዚአብሔርን ፡ በመፍራትና ፡ በመንቀጥቀጥ ፡ በቀሳውስትና ፡ በዲያቆናት ፡ እጅ ፡ ነዳያንን ፡ በእርሷ ፡ የሚመግባቸው ። ዳግመኛም ፡ ከርሷ ፡ ይቀበሉ ፡ ለሚሹ ፡ ወንድሞችና ፡ ለሚጠይቁት ፡ እንግዶች ፡ የሚሹትን ፡ ይስጧቸው ።

፮፻፶፭ ሉቃስ ፡ ሐዋርያትም ፡ ወደእነርሱ ፡ ካመጡላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ እንደሚሻው ፡ ይሰጡአቸው ፡ ነበር ። (የሐዋ ፡ ፬ ፡ ፴፪-፴፭) ።

፮፻፶፮ ጽ፳ ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ በቤተክርስቲያኑ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ይወቀው ። የሚያየው ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳለ ፡ አድርጎ ፡ ይሥራ ፡ ለብቻው ፡ ለማስነገድ ፡ ከእርሷ ፡ ጥቅም ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡ ምንም ፡ ድሆች ፡ ቢሆኑ ፡ የቤተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ገንዘብ ፡ ለዘመዶቹ ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ የሚወዱ ፡ በሆኑ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰዎች ፡ ምክንያት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ገንዘብ ፡ ሊነግድበት ፡ አይገባውም ።

፮፻፶፯ ጾክ ፡ ጽ፰ ፡ ይህን ፡ ባይተው ፡ ለእርሱ ፡ ምግብ ፡ ቢያወጣጣ ፡ ለቤተ ፡ ሰቡም ፡ ቢያወጣጣ ፡ የቤተክርስቲያኑን ፡ ገንዘብ ፡ ለቀሳውስትና ፡ ለዲያቆናት ፡ ባያሳያቸው ፡ ከቤተ ፡ ሰቡ ፡ ጋር ፡ የተለየ ፡ ይሁን ። ነገር ፡ ግን ፡ ቄሱ ፡ ወይም ፡ ዲያቆኑ ፡ አይውጣ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ አይለይ ፡ ስለዚህ ፡ (ማኅበሩ) ፡ ምእመናን ፡ እንዳይጠራጠሩት ።

አንቀጽ ፡ ፲፯ ።

፮፻፶፰ ፰ወ፬ቱ ፡ ወይኩን ፡ ንዋየ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዕዉቀ ፡ በኀበ ፡ ዕዉቃን ፡ ቀሳውስት ፡ ወዲያቆናት ፡ ወከማሁ ፡ ንዋየ ፡ ኤጲስቆጶስኒ ፡ ካዕበ ። ወለእመ ፡ ሞተ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ንዋዩ ፡ ወንዋየ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘዕዉቅ ፡ ኢይትኀጐል ፡ እምኔሆሙ ፡ ምንትኒ ።

፮፻፶፱ ዘዕንቀራ ፡ ፲ወ፬ቱ ፡ ወኵሉ ፡ ንዋየ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘከመ ፡ አልባስ ፡ ወንዋያት ፡ አው ፡ ገራውሀ ፡ አው ፡ ዐፀደ ፡ ወይን ፡ ወእንስሳ ፡ ወዘይመስሎ ፡ ለዝንቱ ፡ ይኩን ፡ ዕቁበ ፡ በእደ ፡ ሕዝብ ፡ ፈራህያነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወምእመናን ።

፮፻፷ ወለእመ ፡ ተዐደወ ፡ ካህን ፡ አው ፡ ካልእ ፡ ከመ ፡ ይሢጥ ፡ እምኔሁ ፡ ንዋየ ፡ ያግብእ ፡ ውእተ ፡ ንዋየ ፡ እምዘሤጠ ፡ ወዘአኀዘ ፡ ዘተሣየጠ ፡ ንዋየ ። ወለእመ ፡ ኢያግብእ ፡ ንዋየ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘሤጠ ፡ ወዘተሣየጠ ፡ ዦነኔሆሙ ፡ ይፍድዩ ፡ ካዕበተ ፡ በመባሕተ ፡ ኤጲስቆጶስ ። ወይግበር ፡ ውስቴቱ ፡ በከመ ፡ ይሬኢ ፡ በፍርሃተ ፡ እግዚአብሔር ።

፮፻፷፩ በስ ፡ ፹ወ፯ቱ ፡ ወለእመ ፡ ሞተ ፡ ፩ዱሂ ፡ ወአዘዘ ፡ ከመ ፡ የሀቡ ፡ ንዋዮ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ውእቱ ፡ ንዋይ ፡ ወርቀ ፡ አው ፡ አልባስ ፡ አው ፡ ብርተ ፡ አው ፡ እክለ ፡ ይንሣእ ፡ መጋቢሁ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ አው ፡ ቀሲስ ፡ ዘቤተ ፡ ክርስቲያን ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ውእቱ ፡ ምንትኒ ፡ ላዕሌሁ ፡ ጸባሕተ ፡ ንጉሥ ፡ አው ፡ ዓሥራት ፡ ኢይትመጠውዎ ። እስመ ፡ ኢመፍትው ፡ ትኩን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በታሕተ ፡ ምልክና።

፮፻፷፪ ክፍል ፡ ዳግማዊ ፡ ከመ ፡ ይሢሙ ፡ መገብተ ፡ ላዕለ ፡ ዘይበውእ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወላዕለ ፡ ዘይወፅእ ፡ እምኔሃ ፡ ወከመ ፡ ይፍልጡ ፡ መካናተ ፡ ለድዉያን ፡ ወለእናግድ ፡ ወይሢሙ ፡ ሎሙ ፡ ላእካነ ። ዘኒቅያ ፡ ፷ወ፯ቱ ፡ ወይሢሙ ፡ ለኵሉ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዐቃቤ ፡ ወመገብተ ፡ ከመ ፡ ይመግቡ ፡ ካዕበ ፡ ለዘይበውእ ፡ ወይወፅእ ፡ ወይትፈለጥ ፡ ለለ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ለግብረ ፡ ዐቂብ ፡ እምእለ ፡ እመገብዎሙ ፡ ይሠየሙ ፡ ቦቱ ፡ በርትዐ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘይደሉ ። ወኢይኩን ፡ ፩ዱሂ ፡ በእምሳለ ፡ ገብር ፡ እኩይ ፡ ዘደፈነ ፡ ወርቀ ፡ እግዚኡ ፡ ዘኢ

በምጽዋት ፡ ገንዘብ ፡ ስለሚሾም ።

፮፻፶፰ ፹፬ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ገንዘብ ፡ በታወቁ ፡ ቀሳውስትና ፡ ዲያቆናት ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ይሁን ። ዳግመኛም ፡ የኤጲስቆጶሱ ፡ ገንዘብ ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። ኤጲስቆጶሱ ፡ ቢሞት ፡ ገንዘቡና ፡ የታወቀ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ገንዘብ ፡ ከእነርሱ ፡ ወገን ፡ ምንም ፡ አይጥፋ ።

፮፻፶፱ ዕንቀራ ፡ ፲፬ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ እንደልብስ ፡ እንደ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ እርሻ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ወይን ፡ ቦታ ፡ እንደ ፡ ከብት ፡ ያለውና ፡ ይህን ፡ የመሳሰለው ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በሚፈሩ ፡ ሰዎችና ፡ በምእመናን ፡ እጅ ፡ የተጠበቀ ፡ ይሁን ።

፮፻፷ ካህኑ ፡ ወይም ፡ ሌላው ፡ ከእሱ ፡ ገንዘቡን ፡ ለመሸጥ ፡ ቢደፋፈር ፡ ከሸጠበት ፡ ይህን ፡ ገንዘብ ፡ ገንዘቡንም ፡ ገዝቶ ፡ የያዘው ፡ ይመልስ ። የሸጠም ፡ የገዛም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ ገንዘብ ፡ ወደቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ባይመልስ ፡ ቅጣታቸው ፡ በኤጲስቆጶሱ ፡ ሥልጣን ፡ እጥፍ ፡ ድርብ ፡ ይከፍሉ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። እግዚአብሔርን ፡ በመፍራት ፡ እንደታየው ፡ ይፍረድ ።

፮፻፷፩ በስ ፡ ፹፯ ፡ አንዱስ ፡ እንኳ ፡ ቢሞት ፡ ገንዘቡን ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዲሰጡ ፡ ቢያዝዝም ፡ ገንዘቡ ፡ ወርቅ ፡ ወይም ፡ ልብስ ፡ ወይም ፡ ብረት ፡ ወይም ፡ እህል ፡ ቢሆን ፡ የኤጲስቆጶሱ ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ቄስ ፡ (ገንዘብ) ፡ ይቀበል ። ምንም ፡ የንጉሥ ፡ ግብር ፡ ወይም ፡ አሥራት ፡ ያለበት ፡ ቢሆን ፡ አይቀበሉት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከግዛት ፡ በታች ፡ ልትሆን ፡ አይገባምና ።

፮፻፷፪ ሁለተኛ ፡ ክፍል ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሚገባውና ፡ ከርሷም ፡ በሚመጣው ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ ሹም ፡ ይሾሙ ፡ ዘንድ ፡ ለሕመምተኞችና ፡ ለእንግዶች ፡ ቦታ ፡ ይለዩ ፡ ዘንድ ፡ አገልጋዮችም ፡ ይሾሙላቸው ፡ ዘንድ ። ኒቅያ ፡ ፷፯ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ጠባቂ ፡ ዳግመኛም ፡ የሚወጣውንና ፡ የሚገባውን ፡ ገንዘብ ፡ ይቆጣጠሩ ፡ ዘንድ ፡ ሹሞች ፡ ይሹሙ ። ከእነሱ ፡ ወገን ፡ ለመጠበቅ ፡ ከሾሟቸው ፡ ወገን ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ይለይ ። በሚገባ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እጋዥነት ፡ ይሾሙ ፡ ዘንድ ። አንዱስ ፡ እንኳ ፡ የጌታውን ፡ ወርቅ ፡ በቀበረ ፡ ነግዶ ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ አም

ነገደ ፡ ቦቱ ፡ ወኢያርብሑ ፡ ፩ደ ፡ አው ፡ ፪ተ ።

፲፻፷፫ ዘ፷ወ፫ቱ ፡ ወይፍልጡ ፡ ለአናግድ ፡ ወለነዳያን ፡ ወለድዉያን ፡ ማኅደረ ፡ በኵሉ ፡ አህጉር ፡ ወለ ይኅረይ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ መነኮሰ ፡ ፈላሴ ፡ ዘር ኁቅ ፡ ብሔሩ ፡ ወሠናይ ፡ ግእዙ ፡ ወያመግብዎ ፡ ይእተ ፡ ዐፀደ ፡ ወኢይርኅቅ ፡ እምነ ፡ ሀገር ፡ ወይንሣእ ፡ ቤተ ፡ ዘይበውእ ፡ ቦቱ ፡ ወያስተ ዳሉ ፡ ውስቴቱ ፡ ዓራታተ ፡ ወመንጸፋተ ፡ ወኵሎ ፡ ዘይትፈቀድ ፡ ለድዉያን ፡ ወለነዳያን ፡ ስፉሐ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ንዋየ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ ያን ፡ ውኑደ ፡ ያስተጋብእ ፡ ሎሙ ፡ ሲሳየ ፡ እም እመናን ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ አምኵሉ ፡ ሰብእ ፡ በአ ምጣነ ፡ ክሂሎቶሙ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ይሠ ረይ ፡ ኃጢአት ፡ ብዙኅ ፡ ወይከውን ፡ ቍርባነ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

፲፻፷፬ ዘ፷ወ፬ቱ ፡ ወይኅረዩ ፡ ሰብእ ፡ ብሔር ፡ በኵሉ ፡ መካን ፡ ፩ደ ፡ ብእሴ ፡ ባሕታዌ ፡ ፍሉጠ ፡ እምሕዝብ ፡ ፀቦቱ ፡ ልሳን ፡ ጥዑሙ ፡ ወዘፍ ኖቱ ፡ ርቱዕ ፡ ወይፍልጡ ፡ ሎቱ ፡ በዓተ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አው ፡ ኀበ ፡ አብያተ ፡ ድዉ ያን ፡ ከመ ፡ ይኅድር ፡ ውስቴቱ ፡ ወይኩን ፡ ንዋ ዮሙ ፡ ዕቁበ ፡ በኀቤሁ ።

፲፻፷፭ ለአናግድሰ ፡ ወለድዉያን ፡ ይኩን ፡ ሊቀ ፡ ሎሙ ዘይዋሕዮሙ ፡ ወየሐውጾሙ ፡ ካዕበ ፡ ለሙቁ ሓን ፡ እምክርስቲያን ፡ ርቱዕ ፡ ወኢይትገበር ፡ ግብረ ፡ ካልእ ፡ ዘእንበለ ፡ አሉ ፡ ዘይፈቅዱ ፡ ወይኅሥሥ ፡ ሎሙ ፡ እምእመናን ፡ ወምእመ ናት ፡ እደው ፡ ወአንስት ፡ ወለዘይፈቅድ ፡ ከመ ፡ ይትሐበይዎ ፡ ለይትሐበዮ ፡ አው ፡ ይኅሥሥ ፡ ሎቱ ፡ ዘይትሐበዮ ። ወለዘሰ ፡ ኮነ ፡ ሀቢየ ፡ አበ ሳሁ ፡ ወአረከበ ፡ ፍኖተ ፡ ለአድኅኖቱ ፡ ወለፈ ቲሖቱ ፡ ያስተሐምም ፡ ሎቱ ፡ መብልዐ ፡ ወል ብሰ ። ወለእመ ፡ ኀጥአ ፡ ፩ዱ ፡ እምእመናን ፡ ዘይፈድዮ ፡ ወለእመ ፡ ኢተክህሎ ፡ እምካልአን ፡ የሀብ ፡ እምዘሎቱ ።

፲፻፷፮ ፀ፯ ፡ ወለእመ ፡ ኀረይዎ ፡ ሕዝብ ፡ ለብእሲ ፡ ትሩፍ ፡ ይኩን ፡ መጋቤ ፡ ለድዉያን ፡ ወኢተሠ ጥወ ፡ በእንተ ፡ ዘይፈቅዱ ፡ እምኔሁ ፡ ይትከላእ እምተሳትፎቱ ፡ ጉባኤ ፡ ወኢይከውኖ ፡ ለ፩ዱኒ፡ ከመ ፡ ይሚጦ ፡ በላዕሌሁ ፡ መጋቤ ፡ እስከ ፡



ስት ፡ ባላተረፈ ፡ በሰነፍ ፡ ባሪያ ፡ አምሳል ፡ አይ ሁን ። ( ማቴ ፡ ፳፭ ፡ ፳፬ - ፴ ) ።

፲፻፷፫ ፷፫ ፡ በሀገሩ ፡ ሁሉ ፡ ለእንግዶች ፡ ለድሆች ፡ ለሕመምተኞች ፡ ማደሪያ ፡ ይለዩ ፡ ኤጲስቆጶ ሱም ፡ ጠባዩ ፡ ያማረውን ፡ አገሩ ፡ እሩቅ ፡ የሆ ነውን ፡ ሰደተኛውን ፡ መነኵሴ ፡ ይምረጥ ። በዚ ያችም ፡ ቦታ ፡ ይሹመው ። ከአገሩ ፡ አይለይ ፡ የሚኖርበትም ፡ ቤት ፡ ይቀበል ፡ በውስጡም ፡ አልጋዎችንና ፡ ምንጣፎችን ፡ ለሕመምተኞ ችና ፡ ለድሆች ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ሁሉ ፡ በስ ፋው ፡ ያዘጋጅ ። የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ገንዘብ ፡ ጥቂት ፡ ቢሆን ፡ ዘወትር ፡ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ችሎታቸው ፡ መጠን ፡ የምእመናንን ፡ ምግብ ፡ ይሰብስብላቸው ። ስለዚህ ፡ ብዙ ፡ ኃጢአት ፡ ይሠረያል ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ መሥዋዕት ፡ ይሆናል ።

፲፻፷፬ ፷፬ ፡ የአገሩ ፡ ሰዎች ፡ በቦታው ፡ ሁሉ ፡ ሥራው፡ የቀና ፡ ልዝብ ፡ አንደበት ፡ ያለውን ፡ ከሕዝቡ ፡ የተለየውን ፡ አንዱን ፡ መነኵሴ ፡ ይሹሙ ። ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወይም ፡ ከድሆች ፡ ቤት ፡ አጠገብ ፡ ቦታ ፡ ይለዩለት ። በውስጡ ፡ ያድር በት ፡ ዘንድ ፡ ገንዘባቸውም ፡ በእሱ ፡ የተጠ በቀ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ።

፲፻፷፭ ለእንግዶችና ፡ ለሕመምተኞች ፡ ግን ፡ የሚያስ ተዳድራቸው ፡ አለቃ ፡ ይሁንላቸው ። ዳግመ ኛም ፡ ከክርስቲያን ፡ ወገን ፡ በቀናች ፡ ሃይማ ኖት ፡ የታሠሩትን ፡ ይጎብኛቸው ። እንዚህ ፡ ከሚሹት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ አይሥራ ። ከወ ንዶችና ፡ ከሴቶች ፡ ምእመናንም ፡ ወገን ፡ ይፈ ልግላቸው ፡ ሊዋሱት ፡ የሚወደውን ፡ ሰው ፡ ዋስ ፡ ይሁነው ። ወይም ፡ የሚዋሰው ፡ ሰው ፡ ይፈልግለት ። በደሉ ፡ ታላቅ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ እርሱን ፡ ለማዳንና ፡ ለማስፈታት ፡ መን ገድ ፡ ባያገኝ ፡ ምግቡንና ፡ ልብሱን ፡ ያስብለት ። ከምእመናን ፡ ወገን ፡ አንዱ ፡ የሚከፍለው ፡ ቢያጣ ፡ ከሌሎችም ፡ ለማግኘት ፡ ባይቻለው ፡ ካለው ፡ ይስጥ ።

፲፻፷፮ ፯ ፡ ሕዝቡ ፡ ለሕመምተኞቹ ፡ ሹም ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ፍጹሙን ፡ ሰው ፡ ቢመርጡት ፡ ከእርሱ ፡ የሚሹትን ፡ ባይወድ ፡ ከማኅበሩ ፡ አንድነት ፡ ይለይ ። እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ ወይም ፡ ከሹመቱ ፡ የሚሻርበት ፡ በደል ፡ እስኪገኝበት ፡ ድረስ ፡

እመ ፡ ይመውት ፡ እው ፡ እመ ፡ አበሰ ፡ ዘየደሉ፡ ባቲ ፡ ፀእት ፡ እመዓርጊሁ ፡ ወለዝንቱስ ፡ ያውግዝዎ ፡ ወይደሉ ፡ ሎቱ ፡ ምግብና ፡ ውእቱኒ ፡ ለእመ ፡ ይክመ ፡ የሀቦ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ መጋቤ ፡ ካልእ ።

፩፻፷፯ በደስ ፡ ዘ፷ወ፰ቱ ፡ ወእስከ ፡ ንዋየ ፡ ልሕኵት ፡ በእንተ ፡ መፍቀደ ፡ ድውያን ፡ የሀቦ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ለመጋቢ ።

፩፻፷፰ ክፍል ፡ ሣልስ ፡ በእንተ ፡ ክፊለ ፡ ምጽዋት ፡ ወውእቱ ፡ ኀበ ፡ ፫ቱ ፡ እክፋል ፡ ቀዳማዊ ፡ ረስጣ ፡ ፬ ፡ ኵሉ ፡ ዓሥራት ፡ ለካህናት ፡ ውእቱ ፡ ወአጋእዝተ ፡ ምጽዋት ።

፩፻፷፱ ወዳግምኒ ፡ እምኔሁ ፡ በኵር ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ቀዳምያት ፡ ይእቲ ፡ ለካህናት ፡ ለባሕቲቶሙ ፡ ወለእለ ፡ ይትለአክዎሙ ።

፩፻፸ ዘ፬ ፡ ወኤጲስቆጶስ ፡ ይንሣእ ፡ ኪያሃ ፡ ወይባርክ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ወይዝክር ፡ ስሞ ፡ ለዘአምጽአ ፡ ሎቱ ፡ በኵረ ፡ ወይበል ፡ ንእኵተከ ፡ አ ፡ እግዚኦ ፡ እስመ ፡ አንተ ፡ አዘዝከ ፡ ለምድር ፡ ከመ ፡ ተሀብ ፡ ኵሎ ፡ ፍሬያተ ፡ ኀበ ፡ መልዕልት ፡ ትፍሥሕተ ፡ ወሲሳየ ፡ ለኵሉ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ወለኵሉ ፡ እንስሳት ። ወለከ ፡ ናቄርብ ፡ ቅድመ ፡ በኵረ ፡ ፍሬያት ፡ ዛቲ ፡ እንተ ፡ ወሀብከነ ፡ ኪያሃ ፡ ከመ ፡ ንሴስይ ፡ እምኔሃ ።

፩፻፸፩ ወዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ፍሬያት ፡ እንተ ፡ ይባርኩ ፡ ላዕሌሃ ፡ ወይን ፡ ወበለስ ፡ ወሮማን ፡ ወዘይት ፡ ወኮል ፡ ወኰኵሕ ፡ ወተፋሕ ፡ ወእልቀራስየ ፡ ወኢይባርኩ ፡ ላዕለ ፡ ሰግላ ፡ ወኢላዕለ ፡ በጸል ፡ ወኢላዕለ ፡ ቱማ ፡ ወኢላዕለ ፡ እልቀጦ ፡ ወሐምሐም ፡ ወላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ዘመደ ፡ በቍላት ፡ ወያብኡ ፡ ካዕበ ፡ ጽጌረዳ ፡ ወካልእንሰ ፡ ኢያብኡ ፡ ወኵሎ ፡ ግብረ ፡ ዘይትበላዕ ፡ ይብልዑ ፡ ወያእኵትዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወየሀቡ ፡ ሰብሐተ ፡ ሎቱ ።

፩፻፸፪ ወሣልስኒ ፡ ዘ፷ወ፩ዱ ፡ ድስቅ ፡ ፷ቱ ፡ ወለዘተርፈ ፡ እምሥጢራት ፡ ዘኢያስረግዎ ፡ ይክፍልዎ ፡ ዲያቆናት ፡ በምክረ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አው ፡ ቀሲስ ፡ ወየሀብዎ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ፬ተ ፡ ክፍለ ፡ ወለቀሳውስት ፡ ፫ተ ፡ ክፍለ ፡ ወለዲያቆናት ፡ ፪ተ ፡ ክፍለ ። ወለካልእንሰ ፡ እምሳለ ፡ ንፉቀ ፡ ዲያቆናት ፡ ወእናጕንስጢስ ፡ ወመዘምራን ፡ ወለዲያቆናውያት ፡ አንስት ፡ የሀብዎሙ ፡ ለኵሉ ፡ ለለ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ በበ፩ዱ ፡ ክፍል ። ወዝ



ለእንዱስ ፡ እንኳ ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ ሹም ፡ ይሾሙ ፡ ዘንድ ፡ አይገባም ። እርሱን ፡ ግን ፡ ነውር ፡ ቢያገኙበት ፡ ያውግዙት ፡ ነውር ፡ ከሌለበትም ፡ በሹመቱ ፡ ይጽና ። እርሱም ፡ ቢደክም ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ ሌላ ፡ ሹም ፡ ይሹምለት ።

፩፻፷፯ በደስ ፡ ፷፰ ፡ ለድውያን ፡ የሚያሻቸውን ፡ እስከ ፡ ሸክላ ፡ ዕቃ ፡ ድረስ ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ ለሹሙ ፡ ይስጠው ።

፩፻፷፰ ሦስተኛው ፡ ክፍል ፡ ምጽዋትን ፡ ስለመክፈል ፡ ይናገራል ። ይኸውም ፡ ከሦስት ፡ ይከፈላል ፡ መጀመሪያው ፡ ረስጣ ፡ ፬ ፡ አሥራት ፡ ሁሉ ፡ ለካህናት ፡ ነው ፡ የምጽዋት ፡ ጌቶች ፡ ናቸውና ።

፩፻፷፱ ሁለተኛው ፡ ከእርሱ ፡ በኵር ፡ ይህችውም ፡ መጀመሪያይቱ ፡ ለካህናትና ፡ ለሚያገለግሏቸውም ፡ ብቻ ፡ ናት ።

፩፻፸ ፬ ፡ ኤጲስቆጶሱም ፡ እርሷን ፡ ተቀብሎ ፡ ይባርካቸው ፡ በኵራቱን ፡ ያመጣለትን ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ይጥራ ። አቤቱ ፡ እናመሰግንሃለን ፡ ይበል ፡ ወደላይ ፡ ደስታን ፡ የሚሆን ፡ የሰው ፡ ሁሉና ፡ የእንስሳትም ፡ ሁሉ ፡ ምግብ ፡ የሚሆን ፡ ፍሬን ፡ ትሰጥ ፡ ዘንድ ፡ አንተ ፡ ምድርን ፡ አዝዘኸታልና ። አስቀድመን ፡ የፍሬዩቱን ፡ መጀመሪያ ፡ እናቀርብልሃለን ። ይህችውም ፡ ከእርሷ ፡ እንመገብ ፡ ዘንድ ፡ እርሷን ፡ የሰጠኸን ፡ ናት ።

፩፻፸፩ ቡራኬ ፡ ሊያደርጉባት ፡ የምትገባ ፡ ፍሬ ፡ ይህች፡ ናት ፡ ወይን ፡ በለስ ፡ ሮማን ፡ ዘይት ፡ እንኮይ ፡ ኮክ ፡ ሙዝ ፡ ሽቱ ፡ በሾላ ፡ በቀይ ፡ ሽንኩርት ፡ በነጭ ፡ ሽንኵርት ፡ በዱባና ፡ በቅል ፡ እነዚህን ፡ በመሳሰሉት ፡ አትክልት ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ አይጸልዩ ። ዳግመኛም ፡ ጽጌረዳ ፡ ያግቡ ። ሌሎችን ፡ ግን ፡ አያግቡ ። የሚበላውን ፡ ምግብ ፡ ሁሉ ፡ ይብሉ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ያመስግኑት ፡ ለእርሱም ፡ ምስጋና ፡ ይስጡ ።

፩፻፸፪ ሦስተኛውም ፡ ፷፩ ፡ ድስቅ ፡ ፷ ፡ ከመሥዋዕት ፡ የተረፈውን ፡ ያልሠዉትን ፡ ግን ፡ ዲያቆናት ፡ በኤጲስቆጶሱ ፡ ወይም ፡ በቄሱ ፡ ፈቃድ ፡ ይክፈሉት ። ለኤጲስቆጶሱ ፡ አራት ፡ ዕጣ ፡ ለቀሳውስት ፡ ሦስት ፡ ዕጣ ፡ ለዲያቆናት ፡ ሁለት ፡ ዕጣ ፡ ይስጧቸው ። ለሌሎች ፡ ግን ፡ ንፉቀ ፡ ዲያቆን ፡ እናጕንስጢስ ፡ መዘምራን ፡ ሴቶች ፡ ዲያቆናውያት ፡ ለመሰሉት ፡ ሁሉ ፡ ከእነርሱ ፡ ወገን ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ሁሉ ፡ አንዳንድ ፡ ዕጣ ፡ ይስጧ...

ንቱ ፡ ሠናይ ፡ ውእቱ ፡ ወውኩፍ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ያከብርዎ ፡ ለኵሉ ፡ ለለ፩ዱ ፡ በበሥርዓቱ ።



ቸው ። ይህ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ እግዚአብሔርም፡ የሚቀበለው ፡ ነው ። ሁሉን ፡ ለእያንዳንዱ ፡ በመዓርጉ ፡ ያከብሩት ፡ ዘንድ ።

## አንቀጽ ፡ ፲ወ፰ቱ ።

በእንተ ፡ ዓሥራት ፡ ወበኵራት ፡ ወብፅዓታት ፡ ወጕልታት ።

፩፻፸፫ ወዝንቱ ፡ ይትከፈል ፡ ኀበ ፡ ፪ቱ ፡ ክፍል ፡ ቀዳሚ ፡ በእንተ ፡ ዘተርፈ ፡ ነገር ፡ እምዓሥራት ፡ ወበኵራት ። ወክፍል ፡ ዳግማዊ ፡ በእንተ ፡ ብፅዓታት ፡ ወጕልታት ፡ ወዝንቱኒ ፡ እምኍልቌ ፡ ምጽዋታት ፡ ክሡታት ።

፩፻፸፬ ቀዳማዊ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትእ ፡ ዘ፱ቱ ፡ ሀቡ ፡ ዓሥራተ ፡ እምኵሉ ፡ እክላቲክሙ ፡ ወአዝርእቲክሙ ፡ ወእምኵሉ ፡ ዘታፈሪ ፡ ምድር ፡ ክሙ ፡ ለለዓመት ። ወበወንጌልኒ፡ ይቤ ፡ "ሀቡ ዘእግዚአብሔር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወዘቄሣር ፡ ለቄሣር ፡ ወአርአየ ፡ በዝንቱ ፡ ቀዛልፎቶሙ ፡ ለፈሪሳውያን ፡ በእንተ ፡ ዘኀደጉ ፡ ፍትሐ ፡ ወምሕረተ ፡ ወሃይማኖተ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ርቱዕ ፡ ትግበሩ ፡ ዘንተ ፡ ወኢትኅድጉ ፡ ዝክተኒ ።

፩፻፸፭ ድሰቅ ፡ ዘ፯ቱ ፡ ወይደልዎ ፡ ለዘይሀመድ ፡ ለመልእክተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከመ ፡ ይንሣእ ፡ እምኔሃ ፡ ኵሎ ፡ መፍቅዶ ፡ ከመ ፡ ካህናት ፡ ወሌዋውያን ፡ ወላእካነ ፡ እግዚአብሔር ፡ በከመ ፡ ጽሑፍ ፡ በመጽሐፈ ፡ ኍልቍ ፡ በእንተ ፡ ካህናት ፡ ይቤሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአሮን ፡ አንተ ፡ ወደቂቅከ ፡ ወአዝማዲከ ፡ ዘትነሥእ ፡ ሀብተ ፡ ዘትትወሀብ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ክህነትክሙ ፡ ወሜምኩከሙ ፡ ከመ ፡ ትዕተቡ ፡ መባእ ፡ ዘይበፅለዋ ፡ ሊተ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ወሀብኩከ ፡ ለከ ፡ ወለደቂቅከ ፡ ከማከ ፡ ለፍሥሐ ። ወኀሊፎ ፡ ንስቲተ ፡ ይቤ ፡ ካዕበ ፡ እስመ ፡ ኵሎ ፡ በኵረ ፡ ዘይት ፡ ወበኵረ ፡ ወይን፡ ወፍሬ ፡ እክል ፡ ወኵሎ ፡ ዘይሁብዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ናሁ ፡ ረሰይኩ ፡ ለከ ፡ ወኵሎ ፡ ፍሬ ፡ ዘተደመ ፡ መጠውኩከ ፡ ወኵሉ ፡ ዘሕሩም ፡ ወኵሉ ፡ በኵር ፡ እምሰብእ ፡ ወእንስሳ ፡ ለከ ፡ ይኩን ፡ ዘሕሩምኒ ፡ ወዘብውሕኒ ።

## አንቀጽ ፡ ፲፰ ።

ስለአሥራት ፡ ስለበኵራት ፡ ስለብፅዓቶች ፡ ስለ ጉልቶች ።

፩፻፸፫ ይኸውም ፡ ከሁለት ፡ ክፍል ፡ ይከፈላል ። መጀመሪያው ፡ ከአሥራትና ፡ ከበኵራት ፡ ስለቀረው ነገር ፡ ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ስለብፅዓቶች ፡ ስለጉልቶች ፡ ይኸውም ፡ ከታወቁ ፡ ምጽዋቶች ፡ ቁጥር ፡ ነው ።

፩፻፸፬ መጀመሪያ ፡ እግዚአብሔር ፡ አለ ። ትእ ፡ ፱ ፡ ከእህላችሁና ፡ ከአትክልታችሁ ፡ ሁሉ ፡ በየዓመቱ ፡ ምድራችሁ ፡ ከምታፈራው ፡ ሁሉ ፡ አሥራት ሰጡ ። (ዘዳግ ፡ ፲፬ ፡ ፳፪) ። በወንጌልም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የቄሣርን ፡ ለቄሣር ፡ ሰጡ ፡ አለ ። ፍርድን ፡ ቸርነትን ፡ ሃይማኖትን ፡ ስለተዉ ፡ በዚህ ፡ ፈሪሳውያንን ፡ እንደዘለፋቸው ፡ አሳየ ፡ ይህንን ፡ ልታደርጉ ፡ ይገባል ፡ ያንንም ፡እትተው ፡ አላቸው ፡(ማቴ ፡ ፳፪ ፡ ፲፰ -፳፪) ።

፩፻፸፭ ድሰቅ ፡ ፯ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ለማገልገል ፡ ለሚተጋ ፡ ሰው ፡ የሚሻውን ፡ ሁሉ ፡ ከእርሷ ፡ መቀበል ፡ ይገባዋል ። እንደ ፡ ካህናት ፡ እንደ ፡ ሌዋውያን ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አገልጋዮች ስለካህናት ፡ በኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፡ እንደተጻፈ ፡ እግዚአብሔር ፡ አሮንን ፡ አንተና ፡ ልጆችህ ፡ ዘመዶችህ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የምትሰጠውን ፡ ሀብት ፡ የምትቀበሉ ፡ ስለክህነታቸው ፡ ነው ፡ አለው ። የእሥራኤል ፡ ልጆች ፡ የሚሳሉልኝን ፡ መባእ ፡ ትጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ሾምኋችሁ ፡ ለደስታም ፡ ይሆንልህ ፡ ዘንድ ፡ ለአንተ ፡ እንደአንተም ፡ ለልጆችህ ፡ ሰጠሁህ ። (ዘኍ ፡ ፲፰ ፡ ፰) ። ጥቂትም ፡ አልፎ ፡ ሁለተኛ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ የዘይቱን ፡ የወይኑንና ፡ የእህሉን ፡ ፍሬ ፡ መጀመሪያ ፡ ሁሉና ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ የሚሰጡትን ፡ ሁሉ ፡ እነሆ ፡ ለአንተ ፡ አድርጌልሃለሁና ፡ የቀደመውን ፡ ፍሬ ፡ ሁሉ ፡ ሰጠሁህ ። የማይበላው፡ ሁሉ ፡ ከሰው ፡ ከእንስሳ ፡ ወገን ፡ በኵር ፡ የሆነው ፡ ሁሉ ፡ የሚበላውም ፡ የማይበላውም ፡ ለአ

፲፻፸፮ በደስ ፡ ፩ወ፳ቱ ፡ ወበዙረ ፡ ፍሬያቲ ፡ ምድርኒ ፡
እምዘሀለዎ ፡ ሎቱ ፡ ለይስድ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስ
ቲያን ። ወቀዳምያተ ፡ ብዕዓታቲሆሙ ፡ ወቀዳ
ምያተ ፡ ምክያዳቲሆሙ ፡ ወቀዳምያተ ፡ ዘይት ፡
ወመዓር ፡ ወሐሊብ ፡ ወፀምር ፡ ወቀዳምያተ ፡
ዓስበ ፡ ግብረ ፡ እደዊሆሙ ፡ ዘንተ ፡ ኵሎ ፡ ያም
ጽኡ ፡ ኀበ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወቀዳምያተ ፡ ፍሬ ፡
ዘዕፀዋቲሆሙ ። ወካህንኒ ፡ ዘይትዌከፍ ፡ ኪያሃ ፡
ያእኵቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በእንቲአሃ ፡ ቅድመ
በአፍአ ፡ እምኒ ፡ መንጦላዕት ፡ እንዘ ፡ ሀለዉ ፡
ቅዉማን ፡ እለ ፡ እምጽእዋ ።

፲፻፸፯ ወዳግም ፡ እስመ ፡ ብዕዓትሰ ፡ በውስተ ፡ ሕግ ፡
ኪዳን ፡ ውእቱ ፡ ዘተካየደ ፡ ብእሲ ፡ ምስለ ፡
ፈጣሪሁ ፡ ለፈጽሞ ፡ ትሩፋት ፡ በርእሱ ፡ እው ፡
በደቂቁ ፡ እው ፡ በንዋዩ ፡ ለእጥርዮ ፡ ኀሠሣ ፡
ሠናይ ፡ እምኀቤሁ ፡ ለልዑል ፡ ሎቱ ፡ ስብ
ሐት ። ወይትናገር ፡ በሕሊናሁ ፡ ወያቅም ፡
ቃላተ ፡ ማእከሌሁ ፡ ወማእከለ ፡ ነፍሱ ፡ እው ፡
ለእመ ፡ ኮነ ፡ ስምዐ ፡ ላዕሌሁ ፡ ዘለሊሁ ፡ ይፈ
ቅዶ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ይፈጽም ብዕዓቶ ፡ ጊዜ ፡
እጥርዮ ፡ ኀሠሣሁ ፡ እምዘነ ፡ ሀለወ ፡ ኀሠሣ ፡
ዚአሁ ። ወባሕቱ ፡ ይከውን ፡ በምንክንያተ ፡
ተንብሎቱ ፡ ለሰማዕት ፡ እው ፡ ለጻድቅ ፡ እው ፡
ዘእንበለ ፡ ተመክዮተ ፡ እሉ ።

፲፻፸፰ ወናሁ ፡ አቅደምነ ፡ ነጊረ ፡ በእንተ ፡ ብዕዓት ፡
እምንዋይ ፡ ወበእንተ ፡ ዘይብዕዕስ ፡ በርእሱ ፡
ዘከመ ፡ ይብዕዕ ፡ ጾመ ፡ ወጸሎተ ፡ እው ፡ ድን
ግልና ፡ ወምንኵስና ፡ እው ፡ ተማኅፆ ፡ እምዕል
ወታቲሁ ፡ ወዝንቱ ፡ በእንተ ፡ ድኂን ፡ እምእ
ኩይ ፡ እው ፡ ለእጥርዮ ፡ ሠናይ ፡ ወእመ ፡ እኮ ፡
በተሐዝቦ ፡ ዘከመ ፡ ግብራተ ፡ ዓለም ፡ እው ፡
እማናዊ ፡ ከመ ፡ ግብር ፡ ዘደኃረ ።

፲፻፸፱ ወበዊስኒ ፡ ወልደ ፡ ትጋ ፡ ፳ወ፫ቱ ፡ መጽ ፡ ፪ወ
፰ቱ ፡ ወዘበፅዐ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወለቤተ ፡
መቅደስ ፡ ተባዕተ ፡ እው ፡ አንስተ ፡ እምደ
ቂቁ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ እመቦ ፡ ብእሲ ፡
ዘበፅዐ ፡ ብዕዓተ ፡ ሤጠ ፡ ነፍሰስ ፡ ለእግዚአብ
ሔር ፡ ወይኩን ፡ ተባዕት ፡ እምወልደ ፡ ፳ ፡
ዓመት ፡ እስከ ፡ ፷ ፡ ዓመት ፡ ፶ ፡ ሰቅል ፡ እምነ ፡
ብሩር ፡ በሰቅለ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ወሤጠ ፡ አን
ስት ፡ ፴ ፡ ሰቅል ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ እመጠነ ፡



ንተ ፡ ይሁን ። (ዘኍ ፡ ፲፰ ፡ ፲፪ - ፲፭) ።

፲፻፸፮ በደስ ፡ ፴፫ ፡ ከአለው ፡ ወገን ፡ የምድርን ፡ ፍሬ
ያት ፡ መጀመሪያ ፡ ወደቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መው
ሰድ ፡ ይገባዋል ፡ የብዕዓታቸውን ፡ መጀመሪያና
የወይኑን ፡ ጭማቂ ፡ የዘይቱንና ፡ የወተቱን ፡
የማምጃውን ፡ የእጃቸውን ፡ ሥራ ፡ ዋጋ ፡ መጀ
መሪያ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ ያምጡ
ከአትክልቶቻቸውም ፡ የፍሬውን ፡ መጀመሪያ ።
እርሷን ፡ የሚቀበለው ፡ ካህንም ፡ ያመጧት ፡
ሰዎች ፡ ቆመው ፡ ሳሉ ፡ ከመጋረጃው ፡ ውጭ ፡
ሁኖ ፡ ስለእርሷ ፡ አስቀድሞ ፡ እግዚአብሔርን ፡
ያመስግነው ።

፲፻፸፯ ዳግመኛም ፡ ብፅዓትስ ፡ ሰው ፡ በራሱ ፡ ወይም ፡
በልጁ ፡ ወይም ፡ በገንዘቡ ፡ ስዕለቱን ፡ ለመፈ
ጸም ፡ በሕግ ፡ ከፈጣሪው ፡ ጋር ፡ የገባው ፡ ቃል
ኪዳን ፡ ነው ፡ እኮ ። ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባ
ውና ፡ ከልዑል ፡ ዘንድ ፡ በጎ ፡ ፍላጎትን ፡ ለማግ
ኘት ። በአሳቡ ፡ ይናገረው ፡ በእግዚአብሔርና ፡
በራሱ ፡ መካከል ፡ ቃሉን ፡ ይወስን ፡ ወይም ፡
የሚሻውን ፡ ነገር ፡ ባገኘ ፡ ጊዜ ፡ ስዕለቱን ፡ ይፈ
ጽም ፡ ዘንድ ፡ የሚወደው ፡ ምስክር ፡ ቢሆነው ፡
እርሱ ፡ የሚሻው ፡ እለና ። ነገር ፡ ግን ፡ በሰማ
ዕቱ ፡ አማላጅነት ፡ ወይም ፡ በጻድቁ ፡ አማላጅ
ነት ፡ ወይም ፡ ያለእነዚህ ፡ አማላጅነት ፡ ይሆ
ናል ።

፲፻፸፰ እነሆ ፡ ከገንዘብ ፡ ወገን ፡ ስለብፅዓት ፡ መናገ
ርን ፡ አስቀደምን ። ስለራሱ ፡ የሚሳለው ፡ ስለ
ለት ፡ ግን ፡ እጾማለሁ ፡ እጸልያለሁ ፡ ወይም ፡
በድንግልና ፡ በምንኵስና ፡ እኖራለሁ ፡ ወይም ፡
ከክፉ ፡ ነገር ፡ እርቃለሁ ፡ ብሎ ፡ የሚሳለው ፡
ስዕለት ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ከክፉ ፡ ለመዳን ፡
ወይም ፡ በጎ ፡ ነገርን ፡ ለማግኘት ፡ ነው ። ይህም
ባይሆን ፡ እንደ ፡ ዓለም ፡ ሥራዎች ፡ በመጠራ
ጠር ፡ ወይም ፡ እንደኋለኛው ፡ ሥራ ፡ በማመን።

፲፻፸፱ ልጅንም ፡ መሳል ። ትጋ ፡ ፳፫ ፡ መጽ ፡ ፪፰ ፡
ከልጆቹ ፡ ውስጥ ፡ ወንዱን ፡ ወይም ፡ ሴትዋን ፡
ለእግዚአብሔርና ፡ ለቤተ ፡ መቅደስ ፡ አገልግ
ሎት ፡ እሰጣለሁ ፡ ብሎ ፡ የተሳለ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡
እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
የነፍስ ፡ ዋጋ ፡ የሚሆን ፡ ስዕለትን ፡ የተሳለ ፡
ሰው ፡ ቢኖር ፡ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡
ስሳ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ያለ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ዋጋ ፡
በቤተ ፡ መቅደሱ ፡ ሚዛን ፡ ከብር ፡ ወገን ፡ ፶

፳፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ወልደ ፡ ፳ ፡ ዓመት ፡ ለይ
ኩን ፡ ሤጠ ፡ ተባዕት ፡ ፳ ፡ ሰቅል ፡ ወሤጠ ፡
አንስት ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ሰቅል ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡
ወልደ ፡ ፩ዱ ፡ ወርኀ ፡ እስከ ፡ ወልደ ፡ ፳ቱ ፡
ዓመት ፡ ይኩን ፡ ሤጠ ፡ ተባዕት ፡ ፳ቱ ፡ ሰቅለ ፡
ብሩር ፡ ወሤጠ ፡ እንስት ፡ ፫ቱ ፡ ሰቅለ ፡ ብሩር ።
ወለእመ ፡ ኮነ ፡ እምወልደ ፡ ፷ ፡ ዓመት ፡ ወዘይት
ሌዓል ፡ እምኔሁ ፡ ይኩን ፡ ሤጠ ፡ ተባዕት ፡ ፲ወ
፭ቱ ፡ ሰቅለ ፡ ብሩር ፡ ወሤጠ ፡ እንስት ፡ ፲ቱ ፡
ሰቅል ።

፮፻፹ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘበፅዐ ፡ ነዳየ ፡ ዘኢይክል ፡
ላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ ሤጥ ፡ ወዳእሙ ፡ በፅዐ ፡
ዘንተ ፡ በጊዜ ፡ ምንዳቤሁ ፡ ለይሑር ፡ ኀበ ፡
ኤጲስቆጶስ ፡ አው ፡ ኀበ ፡ ቀሲስ ፡ ከመ ፡ ያቅም ፡
ላዕሌሁ ፡ ሤጠ ፡ ዘከመ ፡ የእምሩ ፡ እምግብሩ ።

፮፻፹፩ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘበፅዐ ፡ እምነ ፡ እብዕልት ፡
ዘቦቱ ፡ መራዕይ ፡ ወኵሉ ፡ እንስሳ ፡ ወፈቀደ ፡
እግዚእ ፡ ከመ ፡ ይቤዝዎ ፡ በሤጥ ፡ ድልው ፡
ለካህን ፡ ከመ ፡ ያቅም ፡ ሤጠ ፡ ንዋይ ፡ በፍር
ሃተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ ወኢያድሉ ፡
ለገጸ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እስመ ፡ እግዚአብ
ብሔር ፡ ባዕል ፡ ውእቱ ፡ ወያብዕሎሙ ፡ ለእለ ፡
ያመልክዎ ፡ ወውእቱ ፡ ይሁቦሙ ፡ ወርቀ ፡ ወብ
ሩረ ፡ ወመራዕየ ፡ ወምድረ ፡ ወኵሎ ፡ ዘውስ
ቴታ ፡ ወኢይጸንን ፡ ካህን ፡ ኀበ ፡ ብእሲ ፡ ዘበ
ፅዐ ፡ ወኢይፍርሆ ፡ እምኔሁ ፡ ወኢያቅልል ፡
ላዕሌሁ ፡ ወባሕቱ ፡ ይኩን ፡ ኵሉ ፡ መጥኖትክ ፡
ሤጠ ፡ በሰቅለ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ወሰቅልሰ ፡
፩ዱ ፡ ፳ ፡ አቦሊ ፡ ውእቱ ፡ ወበዘከመዝ ፡ እም
ሳል ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይትመጠን ፡ ኵሉ ፡ ብፅዕ
ታት ።

፮፻፹፪ ትዳ ፡ ዘ፲ወ፫ቱ ፡ መጽ ፡ ዘ፪ት ፡ ወእመቦ ፡ ብፅ
ዓት ፡ ዘበፃዕክምዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እግዚእ
ክሙ ፡ ኢትትዐወሩ ፡ ወኢትትሀከዩ ፡ ለፈጽ
ሞቱ ፡ ከመ ፡ ኢይኩን ፡ ላዕሌክሙ ፡ ኃጢአት ፡
በእንቲአሁ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይትኀ
ሠሠ ፡ እምኔክሙ ። ወለእመሰ ፡ ኢተፈቅሩ ፡
ከመ ፡ ትብፅዑ ፡ አልቦ ፡ ኃጢአት ፡ ላዕሌክሙ ፡
ወዘወፅአሰ ፡ እምአፉክሙ ፡ ግበሩ ፡ ወፈጽሙ ፡
በከመ ፡ በፃዕክሙ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እግዚእ
ክሙ ፡ ወዘመተርክሙ ፡ ቢቃለ ፡ አፉክሙ ።

፮፻፹፫ ትዳ ፡ ወብእሲ ፡ ሶበ ፡ በፅዐ ፡ ብፅዓተ ፡ አው ፡
መሐለ ፡ መሐላ ፡ ወእምዝ ፡ ረሰያ ፡ ለነፍሱ ፡ እም



ሰቅል ፡ (ወቄት) ፡ የሴት ፡ ልጅም ፡ ዋጋ ፡ ፴ ፡
ሰቅል ፡ (ወቄት) ፡ ይሁን ፡ አለ ። ከአንድ ፡ ወር ፡
ጀምሮ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ያለ ፡
ልጅ ፡ ቢሆን ፡ የወንዱ ፡ ልጅ ፡ ዋጋ ፡ ፭ ፡ ሰቅል ፡
(ወቄት) ፡ የሴቲቱም ፡ ልጅ ፡ ዋጋ ፡ ፫ ፡ የብር ፡
ሰቅል ፡ (ወቄት) ፡ ይሁን ። ከ፷ ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡
ጀምሮ ፡ ከርሱም ፡ የሚበልጥ ፡ ቢሆን ፡ የወንድ ፡
ልጅ ፡ ዋጋ ፡ ፲፭ ፡ የብር ፡ ሰቅል ፡ (ወቄት) ፡
የሴትም ፡ ልጅ ፡ ዋጋ ፡ ፲ ፡ የብር ፡ (ወቄት) ፡
ይሁን ፡ አለ ። (ዘሌዋ ፡ ፳፯ ፡ ፩ - ፰) ።

፮፻፹ የተሳለውን ፡ ዋጋ ፡ መክፈል ፡ የማይቻለው ፡
ድኃ ፡ ቢሆን ፡ በመከራው ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡
ተሳለ ፡ እንጂ ፡ ችግሩን ፡ እንደሚያውቁ ፡
መጠን ፡ ዋጋውን ፡ ያቀሉለት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡
ኤጲስቆጶስ ፡ ወይም ፡ ወደ ቄስ ፡ ይሂድ ።

፮፻፹፩ የተሳለው ፡ ሰው ፡ መንጋ ፡ ከብት ፡ ሁሉ ፡ ያለው
ከባለጸጎች ፡ ወገን ፡ ቢሆን ፡ ባለቤቱም ፡ በዋጋ ፡
ሊያስቀረው ፡ ቢወድ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመፍ
ራት ፡ ካህኑ ፡ የገንዘቡን ፡ ዋጋ ፡ መወሰን ፡ ይገ
ባዋል ። ለቤተክርስቲያን ፡ አያድላ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ባለጸጋ ፡ ነውና ፡ የሚያመልኩትንም ፡
ያከብራቸዋል ፡ እርሱ ፡ ወርቁንና ፡ ብሩን ፡
መንጋውን ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡
ይሰጣቸዋል ። ካህኑ ፡ የተሳለውን ፡ ሰው ፡ ፊቱን
አይመልከት ። እርሱንም ፡ ፈርቶ ፡ አያቅል
ለት ። ዋጋውን ፡ ሁሉ ፡ መገመትህ ፡ በቤተ ፡
መቅደስ ፡ ሚዛን ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ አንዱ ፡
ሚዛን ፡ ግን ፡ ፳ ፡ አቦሊ ፡ ነው ፡ እንደዚህ ፡
ባለ ፡ መለኪያ ፡ ስዕለቱ ፡ ሁሉ ፡ ሊመጠን ፡ ይገ
ባል ።

፮፻፹፪ ትዳ ፡ ፲፫ ፡ መጽ ፡ ፪ ፡ ለጌታችሁ ፡ ለእግዚአብ
ሔር ፡ የተሳላችሁት ፡ ስዕለት ፡ ቢኖር ፡ ቸል ፡
አትበሉ ፡ ስለእርሱ ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ ኃጢ
አት ፡ እንዳይሆንባችሁ ፡ ለመፈጸም ፡ አትስ
ነፉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእናንተ ፡ ይሻዋልና ።
ልትሳሉ ፡ ባትወዱ ፡ ግን ፡ ኃጢአት ፡ የለባች
ሁም ፡ ከአፋችሁ ፡ የወጣውን ፡ ግን ፡ ሥሩ ፡ ለፈ
ጣሪያችሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንደተሳላችሁ
ትም ፡ አድርጋችሁ ፡ ፈጽሙ ። በእንደበታች
ሁም ፡ ቆርጣችሁ ፡ የተናገራችሁትን ።

፮፻፹፫ ትዳ ፡ ሰው ፡ ስዕለት ፡ ቢሳል ፡ ወይም ፡ መሐላ ፡
ቢምል ፡ ሰውነቱን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ገንዘብ ፡

አንቀጽ ፡ ፲፰ ።

ንዋየ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢይትመየጥ ፡ እምቃሉ ፡ ወኢይኅድግ ፡ ዘወፅአ ፡ እምአፉሁ ።

፲፻፹፬ ወእመኒ ፡ ብእሲት ፡ በሰዐት ፡ ብፅዓተ ፡ ለእግዚ እብሔር ፡ ወረሰየታ ፡ ለነፍሳ ፡ ሕርምተ ፡ ለእግ ዚእብሔር ፡ እመ ፡ ንእሳ ፡ ወይእቲ ፡ እንዘ ፡ ሀለ ወት ፡ በቤተ ፡ አቡሃ ፡ ወሰበ ፡ ሰምዐ ፡ አቡሃ ፡ ኢይዐልጥ ፡ ባቲ ፡ እስመ ፡ ናሁ ፡ ቆመ ፡ ወይ ለወ ፡ ላዕሌሃ ፡ ዘበዕፀት ፡ ወረሰየት ፡ ላዕለ ፡ ነፍሳ ፡ እምሕርመት ።

፲፻፹፭ ወለእመ ፡ ወለጠ ፡ ባቲ ፡ አቡሃ ፡ ወአብጠለ ፡ ቃላ ፡ በዕለተ ፡ ሰምዐ ፡ ኢይጸንዕ ፡ ላዕሌሃ ፡ ዘበ ፅዐት ፡ ወኢዘመተረት ፡ ላዕለ ፡ ነፍሳ ፡ ለእግዚ እብሔር ። ወእግዚእብሔርኒ ፡ ኢይትሐተታ ፡ በዝንቱ ፡ እስመ ፡ አቡሃ ፡ አብጠለ ፡ ቃላ ፡ ወው እቱ ፡ ሥሉጥ ፡ ላዕሌሃ ።

፲፻፹፮ ወእመሰ ፡ ተወሰበት ፡ ይትመየጥ ፡ ግብረ ፡ ብፅ ዓታ ፡ ኀበ ፡ ምታ ፡ እመ ፡ ፈቀደ ፡ ያብጥል ፡ ወእመ ፡ ፈቀደ ፡ ያጽድቅ ፡ ወለእመ ፡ አከልአ ፡ ምታ ፡ ወተፀመመ ፡ እምዝንቱ ፡ በዕለት ፡ ዘሰ ምዐ ፡ ወናሁ ፡ ደለወ ፡ ላዕሌሃ ፡ ኵሉ ፡ ብፅዓት ፡ እንተ ፡ በሰዐት ። ወእመሰ ፡ ተበመማ ፡ በዕለተ ፡ ሰምዐ ፡ ወእሰርአ ፡ እምድኅረ ፡ ውእቱ ፡ ዕለት ፡ ኃጢአት ፡ ትገብእ ፡ ላዕሌሁ ።

፲፻፹፯ ወብፅዓተ ፡ መዓስብለ ፡ ወኅድግት ፡ ሶበ ፡ በፅዓ፡ ወረሰየ ፡ ላዕለ ፡ ነፍሶን ፡ ውእቱ ፡ ይደሉ ፡ ላዕ ሌሆን ።

፲፻፹፰ ወበእንተ ፡ ነገር ፡ ዘጉልት ፡ ናሁ ፡ ሥሩዕ ፡ በእ ንቲአሁ ፡ ላዕለ ፡ ፮ቱ ፡ እክፋል ። ቀዳማዊ ፡ በእንተ ፡ እቅሞተ ፡ ጕልት ። ዳግማዊ ፡ በእንተ፡ ዘይጕልትዎ ። ወሣልስኒ ፡ በእንተ ፡ ዘይጐልቶ። ወራብዕኒ ፡ በእንተ ፡ ዘይጐልቱ ፡ ሎቱ ። ወኃ ምስኒ ፡ በእንተ ፡ ዘይሠየም ፡ ወበእንተ ፡ ዘይከ ውን ፡ ሰብእ ፡ ዓይነ ፡ ላዕለ ፡ ዘይሠየም ፡ ወሳድ ስኒ ፡ በእንተ ፡ ፍጻሜ ፡ ትእዛዛት ።

፲፻፹፱ ጕልትሰ ፡ ይትከፈል ፡ ኀበ ፡ ፪ቱ ፡ ሀብት ፡ ወም ጽዋት ። ቀዳማዊ ፡ ጕልቶ ፡ ለዘኢኮነ ፡ ነዳየ ፡ በጊዜ ፡ ይጐልቱ ፡ ሎቱ ፡ ዘከመ ፡ ወልድ ፡ ወዘመድ ፡ ወቢጽ ፡ ወዝንቱ ፡ ሀብት ፡ ውእቱ ፡ ዘይትፈቀድ ፡ ቦቱ ፡ በቀኖናት ፡ ለገቢረ ፡ ኀበ ፡ ኀሣሠ ፡ ገበር ፡ ሠናይ ፡ በዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ወፋ ድፋደ ፡ ሶሚት ፡ በደኃሪት ፡ ዓለም ።

፲፻፺ ዳግማዊሰ ፡ ዘይጕልትዎ ፡ ለጽኑሳን ፡ ብዙሕ ፡

ስለ ፡ ዓሥራት ።

ካደረጋት ፡ በኋላ ፡ ቃሉን ፡ አይለውጥ ፡ ከአ ፉም ፡ የወጣውን ፡ አይተው ።

፲፻፹፬ ሴትም ፡ ከትንሽነቷ ፡ ጀምራ ፡ ሰውነቷን ፡ ለእ ግዐአብሔር ፡ የተለየ ፡ አድርጋ ፡ ለእግዚአብ ሔር ፡ ስዕለት ፡ ብትሳል ፡ ይህችውም ፡ በአባቷ ፡ ቤት ፡ ሳለች ፡ ነው ። አባቷ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ስዕ ለቷን ፡ እያፍርስባት ፡ ከመለየት ፡ ወገን ፡ በሰው ነቷ ፡ ላይ ፡ ያያረገችውን ፡ የተሳለችውንም ፡ መፈጸም ፡ ይገባልና ።

፲፻፹፭ አባቷ ፡ ቢለውጥባት ፡ በሰማም ፡ ጊዜ ፡ ቃሏን ፡ ቢያፈርስባት ፡ በሰውነቷ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቆርጣ ፡ የተሳለችው ፡ ስዕለት ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ አይጸናም ። በዚህም ፡ እግዚአብሔር ፡ አይፈር ድባትም ። አባቷ ፡ ቃሏን ፡ አፍርሶባታልና ፡ እርሱም ፡ በእርሷ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ አለውና ።

፲፻፹፮ ብታገባ ፡ ግን ፡ የስዕለቷ ፡ ሥራ ፡ ወደባሏ ፡ ይመ ለሳል ፡ ሊያፈርስ ፡ ቢወድ ፡ ሊያጸናም ፡ ቢወድ። በሰማበት ፡ ቀን ፡ ይህን ፡ ችላ ፡ ብሎ ፡ ባይከለከ ላት ፡ እነሆ ፡ የተሳለችውን ፡ ስዕለት ፡ ሁሉ ፡ መፈጸም ፡ ይገባታል ። በሰማበት ፡ ቀን ፡ ችላ ፡ ቢላት ፡ ግን ፡ ከዚያ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ቢያፈርስ ባት ፡ ኃጢአት ፡ ወደርሱ ፡ ትመለሳለች ።

፲፻፹፯ ባል ፡ የሌላትና ፡ በነውር ፡ የተፈታችው ፡ ሴት ፡ ስዕለት ፡ ግን ፡ በሰውነታቸው ፡ የተለዩ ፡ ሁነው ቢሳሉ ፡ መፈጸም ፡ ይገባቸዋል ።

፲፻፹፰ ስለ ፡ ጉልት ፡ ነገር ። እነሆ ፡ ስለርሱ ፡ በስድስት፡ ክፍል ፡ ተጽፏል ። መጀመሪያ ፡ ጉልት ፡ ስለመ ጎለት ፡ ሁለተኛው ፡ ስለሚጐልቱት ፡ ጉልት ፡ ሦስተኛውም ፡ ስለሚጐልተው ፡ አራተኛውም፡ ስለሚጐልቱለት ፡ አምስተኛውም ፡ ስለሚሾመ ውና ፡ በተሾመው ፡ ላይ ፡ ጉበኛ ፡ ስለሚሆነው ፡ ስድስተኛውም ፡ ስለትእዛዛቱ ፡ ፍጻሜ ።

፲፻፹፱ ጉልት ፡ ግን ፡ ከሁለት ፡ ይከፈላል ። ሀብትና ፡ ምጽዋት ። መጀመሪያ ፡ በሚጐልቱለት ፡ ጊዜ ፡ ድኃ ፡ ላልሆነ ፡ መጐለት ፡ ነው ። እንደልጅ ፡ እንደ ፡ ዘመድ ፡ እንደ ፡ ባልንጀራ ፡ ያለ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ለተጠሩት ፡ ሰዎች ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በመጨረሻውም ፡ ዓለም ፡ ዋጋ ፡ ለማብዛት ፡ በጎ ፡ ስምንም ፡ ለማትረፍ ፡ ጥቅም ፡ የሚሻበት ፡ ሀብት ፡ ነው ።

፲፻፺ ሁለተኛው ፡ ግን ፡ ለተቸገሩ ፡ ሰዎች ፡ የሚጐል

አንቀጽ ፡ ፲፰ ፡፡

እመኒ ፡ ኮኑ ፡ ነኪራነ ፡ እው ፡ አዝማደ ፡ ወው
እቱ ፡ ዘይትፈቀድ ፡ በዝንቱ ፡ አንቀጽ ፡ ወዝ
ንቱሰ ፡ ይከውን ፡ ምጽዋተ ፡ ዘይፈቅዳ ፡ ወሃቢ ፡
እስመ ፡ በጕልቆቱ ፡ ቦቱ ፡ በቀኖዔት ፡ ለጽኑ
ሳን ፡ በዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ዘያእዜ ፡ ወአዝልፎተ ፡
በቀኖዔትሰ ፡ ወዕሴት ፡ በዓፀድ ፡ ደኃራዊ ፡፡ ወይ
እቲ ፡ ምጽዋት ፡ ትርፍት ፡ ዘትትነገር ፡ በእንተ፡
በቀኖዔት ፡ እመኒ ፡ በሞቱ ፡ እው ፡ በሕይወቱ ፡
ወለእሙ ፡ ኮነ ፡ ዓጽፈ ፡ ኃጣውእ ፡ ትተልዎ ፡
ለብእሲ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡
ዘውእቱ ፡ ኵሉ ፡ ዘየሐግግ ፡ ሕገ ፡ እኩየ ፡ ወይተ
ርፍ ፡ ግብሩ ፡ እምድኅረ ፡ ሞቱ ፡ ወእፎ ፡ ፊድ
ፋደ ፡ ይደሉ ፡ በርትዐ ፡ እግዚአብሔር ፡ በም
ግባረ ፡ ሠናይ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ዓስበ ፡ ምግባር ፡
ሠናይት ፡ ዘትተርፍ ፡ እምድኅረ ፡ ፈሊሶቱ ፡
ወትትልዎ ፡ ለገባሪሃ ፡፡

፮፻ ፶፩ ወበእንተ ፡ ግብርሂ ፡ ዘይጐልቆ ፡ ወውእቱኬ ፡
እስመ ፡ ኵሉ ፡ ግብር ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡
ዘይትከሀል ፡ ለበቀኖዔት ፡ ለእለ ፡ ይበቍዖሙ ፡
ምስለ ፡ ንብረት ፡ አኮ ፡ ከመ ፡ ዲናር ፡ ወደራ
ህም ፡ ወፈድፋደስ ፡ ኢይኩን ፡ ዘእንበለ ፡ ዘይ
ትከሀል ፡ ለከዊነ ፡ በቀኖዔት ፡ ዘዘልፈ ፡ ይሄሉ ፡
ወዘኢይትከሀል ፡ ለእፍልሶ ፡ ዘከመ ፡ ሕንጻ ፡
ወገራህት ፡ ወሐቅል ፡ ወዘይመስሎ ፡ ለዝንቱ ፡
በከመ ፡ ተዘክረ ፡ በቀኖናት ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡
ይኩን ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡፡ ወዘሂ ፡ ዘኢይት
ጋባእ ፡ ውስቴታ ፡ ዘከመ ፡ ገራህት ፡ ዘኮነ ፡
በደጠ ፡ ዘኢትትቄነፍ ፡ ተገብሮ ፡ ወኢይትበ
ቋዕ ፡ ባቲ ፡ ነባሪሃ ፡ ወኢይትከሀል ፡ እፍል
ሶታ ፡፡

፮፻ ፶፪ ወከማሁ ፡ ውእቱኒ ፡ ዘከመ ፡ አግብርት ፡ ወእን
ስሳ ፡ ወንህብ ፡ እስመ ፡ እሉ ፡ ኵሎሙ ፡ ኢያዘ
ልፉ ፡ ንብረተ ፡ ወይከውን ፡ ተኃጥእቶሙ ፡ ሶበ፡
ይሰርቅዎሙ ፡ ወሶበሂ ፡ ይጐይዩ ፡ ወዘይመ
ስሎ ፡ ለዝንቱ ፡ ከዊነ ፡ ተግኅሥቶሙ ፡፡

፮፻ ፶፫ ወለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ይጐልት ፡ ምንተኒ ፡ እምነ ፡
እሉ ፡ ድልው ፡ ወይፈደፍድ ፡ ከመ ፡ ይሣጥ ፡
ወይሣየጥ ፡ በሤጠ ፡ ዘእሁ ፡ ዘይደሉ ፡ ተረ
ፈታ ፡ ወተግባረ ፡ በቀኖዔትኒ ፡ ይከውን ፡ እም
ኔሃ ፡ ወእመሰ ፡ ኮኑ ፡ አግብርት ፡ ወአልሕምት ፡
[illegible] ፡ እም[illegible] ፡ ሕንጻ ፡ ዓፀድ ፡ ወፈ

ስለ ፡ ዓሥራት ፡፡

ቱት ፡ የሚገባ ፡ ነው ፡ ምንም ፡ ባዕዶች ፤ ወይም
ዘመዶች ፡ ቢሆኑ ፡ ይኸውም ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡
የሚወደድ ፡ ነው ፡፡ ይህ ፡ ግን ፡ ሰጭ ፡ የሚሻው ፡
ምጽዋት ፡ ይሆናል ፡፡ ዛሬ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ለተቸ
ገሩ ፡ ሰዎች ፡ በመጕለቱ ፡ ጥቅም ፡ ይገኝበታ
ልና ፡ ጥቅምና ፡ ዋጋ ፡ ማግኘት ፡ ግን ፡ በወዲ
ያኛው ፡ ዓለም ፡ ነው ፡፡ ይህችውም ፡ ስለጥቅም ፡
የምትነገር ፡ ትርፍ ፡ ያላት ፡ ምጽዋት ፡ ናት ፡፡
በሞቱ ፤ ወይም ፡ በሕይወቱ ፡ ቢሆን ፡ ሰውየው
ን ፡ ኃጢአቱ ፡ እጥፍ ፡ ድርብ ፡ ሆና ፡ የምትከተ
ለው ፡ ቢሆን ፡ ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ እንደተና
ገረ ፡ ይኸውም ፡ ክፉ ፡ ሥራን ፡ ሁሉ ፡ የሚሠራ፡
ነው ፡፡ ከሞተም ፡ በኋላ ፡ ሥራው ፡ ይቀራል ፡፡
በእግዚአብሔር ፡ አጋዥነት ፡ በበጎ ፡ ሥራ ፡
ከሞት ፡ በኋላ ፡ የምትቀር ፡ የበጎ ፡ ሥራው ፡
ዋጋ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ሠሪዋንም ፡ ትከተለው ፡
ዘንድ ፡ ፈጽሞ ፡ እንዴት ፡ ይገባል ፡፡

፮፻ ፶፩ ስለሚጐለተውም ፡ ሥራ ፡ ይኸውም ፡
ሥራው ፡ ሁሉ ፡ ከገንዘቡ ፡ ጋራ ፡ ለሚጠቅማ
ቸው ፡ ሰዎች ፡ ጥቅም ፡ ያለው ፡ ሊሆን ፡ ይገ
ባል ፡ እኮ ፡፡ እንደ ፡ ዲናር ፡ እንደ ፡ ድርሀም ፡
(ጥሬ ፡ ገንዘብ) ፡ ያለውን ፡ አይደለም ፡ ይልቁ
ንም ፡ ዘወትር ፡ ጥቅም ፡ የሌለበት ፡ ሊሆን ፡ አይ
ገባም ፡ ሊያፈልሱት ፡ የማይቻል ፡ እንደ ፡ ሕንፃ፡
እንደ ፡ እርሻ ፡ እንደ ፡ አትክልት ፡ ይህንንም ፡
እንደመሰለ ፡ ያለውን ፡ ነው ፡፡ እርሱ ፡ ለቤተ ፡
ክርስቲያን ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ በመጻሕፍት ፡ እን
ደተነገረ ፡፡ በውስጧ ፡ ሰብል ፡ የማይገኝባትን ፤
ምድረ ፡ በዳ ፡ የሆነችውን ፡ ለእርሻ ፡ የማትሆን ፡
ሰነዋሪ ፡ የማትጠቅመውን ፡ ሊያዛውሩዋትም ፡
የማይቻለውን ፡ ግን ፡ አይጐልቱ ፡፡

፮፻ ፶፪ እንደዚሁም ፡ ይኸውም ፡ እንደባሪያ ፤ እንደ ፡
ከብት፡ እንደንብ ፡ ያለው ፡ ነው ፤ እነዚህ ፡ ሁሉ፡
ዘወትር ፡ አይኖሩምና ፡ አይጐልቷቸው ፡ በሰረ
ቋቸው ፡ ጊዜ ፡ በከዱም ፡ ጊዜ ፡ ይህንም ፡ በመ
ሰለው ፡ ጊዜ ፡ መታጣታቸው ፡ ይሆናል ፡፡
መሄድ ፡ የሚቻላቸው ፡ ስለሆነ ፡፡

፮፻ ፶፫ ከእነዚህ ፡ ማናቸውንም ፡ ሊጐልት ፡ ቢወድ ፡
ይገባል ፡፡ ይሸጥ ፡ ይለውጥ ፡ ዘንድ ፡ በዋጋው ፡
ትርፍ ፡ ያለበትን ፡ ያበዛል ፡ የጥቅምም ፡ ሥራ ፡
ከርሷ ፡ ይገኛል ፡ ከቦታው ፡ ሕንፃ ፡ ቍጥር ፡
ወገን ፡ ባሪያዎች ፡ ላሞች ፡ ገንዘቦች ፡ ቢሆኑ ፡
ግን ፡ ጌታቸው ፡ በውስጧ ፡ ካለው ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡

ቀደ ፡ መላኪሆሙ ፡ ከመ ፡ ይጐልት ፡ ያእተ ፡
ሀገረ ፡ ሕንጽተ ፡ ምስለ ፡ ኵሉ ፡ ዘውስቴታ ፡
ሠናይ ፡ ከመ ፡ ይጐልት ፡ ዘኢይፈልስ ፡ ወከመ፡
ይኩን ፡ ገዛኢ ፡ በዘኢይፈልስ ፡ ላዕለ ፡ ፍኖተ ፡
ምጽዋት ፡ ከመ ፡ ይትመገብ ፡ ቦቱ ፡ በሤጥ ፡
ወዘይመስሎ ፡ በአምጣነ ፡ ዘይትረአይ ፡ አምሠ
ናያት ።

፲፱ ፺፬ ፫ቱ ፡ ወዘኒ ፡ ይጐልቶ ፡ ኢይኩን ፡ ዘአንበለ ፡
ዘብዉሕ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይትመገብ ፡ ቦቱ ፡ እም
ንዋየ ፡ ዚእሁ ፡ በከመ ፡ ተነግረ ፡ በእብጥሊ
ሳት ፡ ኀበ ፡ ይፈልጥ ፡ እንቀጸ ፡ ውሂብ ። ወበእ
ንተ ፡ ትእዛዛት ፡ ኵሎን ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ብእሲ፡
በጊዜ ፡ ጐልቶቱ ፡ ብጹሐ ፡ እምጣን ፡ ወማእ
ምረ ፡ ወግዑዘ ፡ ወኅሩየ ፡ ወሰላማዌ ፡ በግብሩ ፡
ወሠናየ ፡ በልቡ ።

፲፱ ፺፭ ፬ቱ ፡ ወዘሂ ፡ ይጐልቱ ፡ ሎቱ ፡ ኢይደሉ ፡
ከመ ፡ ይኩን ፡ እምእለ ፡ ተግህጹ ፡ በወፂአ ፡
እምትእዛዛት ፡ እምላካውያን ፡ ኢ ፡ በሃይማ
ኖት ፡ ከመ ፡ መጥዓውያን ፡ ወፈድፋደሰ ፡ ኢይ
ኩን ፡ እምእለ ፡ ያመልኩ ፡ ካልአ ፡ እምእግዚአ
ብሔር ፡ ወኢ ፡ በምግባራቲሁ ፡ ከመ ፡ ጸናሕ
ያነ ፡ ፍኖት ፡ ወኃጥእን ፡ እለ ፡ የሐውሩ ፡ ወእለ፡
የሐውርዎሙ ። ወለእመ ፡ ተመይጠ ፡ ዝንቱ ፡
እምነ ፡ ከሕደቱ ፡ ወካልአ ፡ እምእከዩ ፡ ወተጠ
የቀ ፡ ተመይጦቱ ፡ ይንሣእ ፡ ዘተጐለተ ፡ ሎቱ ፡
ወኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ዐብደ ፡ ወዘኢይትአ
መር ፡ ወዘኢይበቍዕ ፡ ለዘይጐልትዎ ፡ ሎቱ።

፲፱ ፺፮ ፭ቱ ፡ ወዘይሠየምዎ ፡ ላዕለ ፡ ጐልት ፡ ዘኀረዮ ፡
ዘይጐልት ፡ ይሢም ፡ በሕይወቱሂ ፡ ወእምድኅረ
ሞቱሂ ፡ ወለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ጐላቲ ፡ ከመ ፡ ይሠ
የም ፡ ዲበ ፡ ዘጐለተ ፡ እስከ ፡ ጊዜ ፡ ሞቱ ፡ ይደ
ልዎ ፡ ለእመ ፡ ወሰነ ። ወለእመሰ ፡ ኢያጠየቀ ፡
መላኪ ፡ ኢ ፡ ለርእሱ ፡ ወኢ ፡ ለካልእ ፡ ለይሠ
የም ፡ ዘተጐለተ ፡ ሎቱ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ድልወ ፡
ለዝንቱ ፡ ወእመ ፡ አኮሰ ፡ መኰንን ፡ ይሢም ፡
ዘኀረየ ፡ ወይሢም ፡ ላዕሌሁ ፡ ሰብእ ፡ ዓይን ፡
ወሰብአ ፡ ዓይንሰ ፡ ላዕለ ፡ ሥዩም ፡ ውእቱኬ ፡
ኤጲስቆጶስ ፡ በውእቱ ፡ ጊዜ ።

፲፱ ፺፯ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘተወፈየ ፡ ጐላቲ ፡ ውእቱ ፡
አው ፡ ካልኡ ፡ ይደልዎ ፡ ለሰብእ ፡ ዓይን ፡ ከመ፡
ይሥዓሮ ፡ ለዘተወፈየ ፡ ምግብናሁ ፡ ለጐልት ፡
ለእመ ፡ ተጠየቀ ፡ እማስኖቱ ፡ በሰማዕት ፡ ወለ



የቀናችውን ፡ እዛር ፡ ሊጐልት ፡ ቢወድ ፡ እንዳ
ይፈልስ ፡ አድርጎ ፡ መጐለት ፡ ይገባዋል ። የተ
ጐለተለት ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ምጽዋት ፡ መንገድ ፡ እን
ዳይሄድ ፡ ሽጦ ፡ በሚመስለውም ፡ ይመገብበት ፡
ዘንድ ፡ ከበጎ ፡ ወገን ፡ እንደተገለጠ ፡ መጠን ።

፲፱ ፺፬ ፫ ፡ የሚጐልተው ፡ ሰው ፡ በገንዘቡ ፡ ያዝበት ፡
ዘንድ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አይ
ጐልት ፡ የስጦታን ፡ አንቀጽ ፡ በሚለይ ፡ በሲኖ
ዶስ ፡ (እብጥሊስ) ፡ እንደተነገረው ። ስለትእዛ
ዛት ፡ ሁሉ ፡ ሰው ፡ በሚጐልትበት ፡ ጊዜ ፡
እካለ ፡ መጠን ፡ ያደረሰ ፡ እዋቂ ፡ ራሱን ፡ የሚ
ገዛ ፡ የተመረጠ ፡ በሥራው ፡ ሰላማዊ ፡ በልቡ ፡
ያማረ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ።

፲፱ ፺፭ ፬ ፡ የሚጐልቱለት ፡ ሰው ፡ ከእምላካውያን ፡
ትእዛዞች ፡ በመውጣት ፡ ከተገለጡት ፡ ሰዎች ፡
ወገን ፡ ሊሆን ፡ አይገባም ። በሃይማኖት ፡ ጣዖት
እንደሚያመልኩ ፡ ይልቁንም ፡ ከእግዚአብሔር
ይልቅ ፡ ሌላውን ፡ ከሚያመልኩ ፡ ወገን ፡ አይ
ሁን ። በሥራውም ፡ ብኀዳና ፡ ሽምቀው ፡ እን
ደሚቆዩ ፡ ግብረ ፡ ሰዶም ፡ እንደሚሠሩ ፡ እንደ
ሚሠሩዋቸውም ፡ ኃጥአን ፡ መሆን ፡ አይገባ
ውም ። ይህ ፡ ከክህደቱ ፡ ሌላውም ፡ ከክፋቱ ፡
ቢመለስ ፡ መመለሱ ፡ ቢረዳ ፡ የተጐለተለትን ፡
ይውሰድ ። ሰነፍ ፡ የማይታወቅ ፡ ለጐለቱለት ፡
ጉልት ፡ የማይጠቅም ፡ መሆን ፡ አይገባውም ።

፲፱ ፺፮ ፭ ፡ በጉልቱ ፡ ላይ ፡ የሚሾመውም ፡ ሹም ፡ የሚ
ጐልተው ፡ ሰው ፡ የመረጠው ፡ በሕይወቱም ፡
ከሞቱም ፡ በኋላ ፡ ቢሆን ፡ ይሹም ። ጐላች ፡
እስከሚሞትበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ በጐለተው ፡
ጉልት ፡ ላይ ፡ ሊሾም ፡ ቢወድ ፡ ጊዜ ፡ ከወሰነ ፡
መሾም ፡ ይገባዋል ። ገዢው ፡ ለራሱ ፡ ለሌላም ፡
ቢሆን ፡ ካላስረዳ ፡ ግን ፡ የተጐለተለት ፡ ሰው ፡
ለዚህ ፡ የተገባ ፡ ቢሆን ፡ ይሾም ። የተገባ ፡ ባይ
ሆን ፡ ግን ፡ ሹሙ ፡ የመረጠውን ፡ ይሹም ፤ ጉበ
ኛም ፡ (ተቆጣጣሪ) ፡ ይሹምበት ፡ በዚያን ፡ ጊዜ
ም ፡ በሹሙ ፡ ላይ ፡ ጉበኛ ፡ (ተቆጣጣሪ) ፡ የሆ
ነው ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ ነው ።

፲፱ ፺፯ የተቀበለው ፡ ጐላቹ ፡ ወይም ፡ የተጐለተለት ፡
ቢሆን ፡ ጥፋቱ ፡ በምስክር ፡ ከተረዳ ፡ ኤጲስቆ
ጶሱ ፡ (ጉበኛው) ፡ የጉልቱን ፡ ሹመት ፡ የተቀበ
ለውን ፡ ሰው ፡ ሊሽረው ፡ ይገባዋል ። ጥፋቱ ፡

አንቀጽ ፡ ፲፰ ።

እመ ፡ ተከሥተ ፡ ዝንቱ ፡ ይወልጥ ፡ ኲልአ ፡ ዘተ
ግህደ ፡ በተአምኖቱ ፡ ወዘይበቍዕሂ ።

፯፻ ፺፰ ወበከመ ፡ ኢይደልዎ ፡ ለዘተሠይመ ፡ ምግብ
ናሁ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ምንተኒ ፡ ባሕቲቱ ፡ ዘእን
በለ ፡ ስብእ ፡ ዓይን ፡ ዘላዕሌሁ ፡ ወከማሁ ፡ ኢይ
ደልዎ ፡ ለሰብእ ፡ ዓይን ፡ ይግበር ፡ ምንተኒ ፡
ዘእንበለ ፡ ምስለ ፡ ዘተሠይመ ፡ ወይግበሩ ፡
ዘንተ ።

፯፻ ፺፱ ወዘያኤምርስ ፡ ላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ በከመ ፡ ተነግረ ፡
ዘቀኖናት ፡ በአንቀጸ ፡ መጋቢ ፡ ምጽዋት ፡
ዘከመ ፡ ይቤሉ ፡ እመሰ ፡ ተአመነ ፡ ላዕለ ፡ ነፍ
ሳቲ ፡ ሰብእ ፡ ክቡራት ፡ ወምንትኬ ፡ ይእቲ ፡
ኮሳ ፡ ጥሪታት ፡ እንተ ፡ ትትወሀብ ፡ ሎቱ ፡
ይመግብ ፡ ኪያሃ ፡ በትእዛዘ ፡ ዚአሁ ። ወብሂሎ
ቶሙ ፡ ኮሉ ፡ ንዋይ ፡ ዘቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ይኩን ፡ ሰቁበ ፡ በእደ ፡ ሰብእ ፡ ምእ
መናን ፡ ወፈራህያን ፡ እግዚአብሔር ፡ ወበዘይመ
ስሎሙ ።

፰፻ ጌቱ ፡ ወፍጻሜ ፡ ትእዛዛትስ ፡ ፲ቱ ፡ እሙንቱ ፡
ቀዳሚ ፡ ከመ ፡ ኢይሣእ ፡ እምእደ ፡ ዘጎሎቱ ፡
ሎቱ ፡ እስከ ፡ ይመውት ፡ ወኢይሣእ ፡ ፩ዱሂ ፡
እምዘቆመ ፡ ላዕሌሁ ፡ እስከ ፡ ይመውት ፡ ወኢይ
ሚጥ ፡ ምንተኒ ፡ እምኔሁ ። ወእመኒ ፡ ተሠይጠ ፡
ይግባእ ፡ ሚጡ ፡ በከመ ፡ ተሠርዐ ፡ በአንቀጸ ፡
መጋቢ ፡ ምጽዋት ። ወይደሉ ፡ ከመ ፡ ኢየሀብዎ፡
ወኢይትወከፍዎ ፡ ወኢያስተአኅዝዎ ፡ ወኢየአ
ኅዝዎ ፡ ወኢይመጽውቱ ፡ ቦቱ ፡ ወኢይሥርዑ ፡
ውስቴቱ ፡ ዘእንበለ ፡ በዘይደሉ ።

፰፻፩ ወዳግምኒ ፡ ወይኩን ፡ ሥርዓተ ፡ ውሳኔሁ ፡ ለዘ
ተጎለተ ፡ በከመ ፡ ተነግረ ፡ በአንቀጸ ፡ አብጥ
ሊስ ፡ ዘውሂበ ፡ ምጽዋት ፡ ዘውእቱ ፡ ሥርዓተ ፡
ውሳኔሁ ፡ እንተ ፡ ኢይከልእ ፡ ሥርዓተ ፡ ዚአሁ፡
ዘውእቱ ፡ ረኪበ ፡ በቍዔት ፡ እምኔሃ ፡ ዘልፈ ።

፰፻፪ ወሣልስኒ ፡ ወለእመ ፡ ተጎለተ ፡ ለዘንጉደ ፡ ወተ
ዐውቀት ፡ ተ፡ንጥአቱ ፡ እምቅድመ ፡ ይጽሐፉ ፡
ሎቱ ፡ ሥርዓተ ፡ ጉልቶ ፡ ይግባእ ፡ ለቤተ ፡ ክር
ስቲያን ፡ ወተአዘዘ ፡ በእንቲአሁ ፡ ከመ ፡ ይኩን፡
ለጽኑሳን ፡ ለባሕቲቶሙ ፡ በከመ ፡ ተነግረ ፡
በእንተ ፡ ጕልት ፡ ወካልኡ ። ።

ስለ ፡ ዓሥራት ።

ከታወቀ ፡ ርሱን ፡ ሽሮ ፡ በታማኝነቱ ፡ የታወቀ
ውን ፡ የሚጠቅመውንም ፡ ሌላውን ፡ ይሹም ፡
በርሱ ፡ ላይ ፡ ከተሾመው ፡ ከኤጲስቆጶሱ ፡
(ጉበኛ) ፡ ጋር ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፯፻ ፺፰ አስተዳደሩን ፡ የተሾመው ፡ ብቻውን ፡ ምንም ፡
ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ እንደማይገባው ፡ እንደዚሁም ፡
ኤጲስቆጶሱ ፡ ከተሾመው ፡ ጋር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡
ብቻውን ፡ መሥራት ፡ አይገባውም ፡ ይህንንም ፡
ያድርግ ።

፯፻ ፺፱ በዚህ ፡ ላይ ፡ የሚያስረዳ ፡ ግን ፡ በአንቀጸ ፡
መጋቢ ፡ ምጽዋት ፡ በመጻሕፍት ፡ እንደ ተነገረ ፡
ነው ። እንዲህ ፡ እንዳሉ ፡ ክቡራት ፡ በሚሆኑ ፡
በሰዎች ፡ ሰውነቶች ፡ ላይ ፡ ቢታመን ፡ ግን ፡
በርሱ ፡ ፈቃድ ፡ ያስተዳድርባት ፡ ዘንድ ፡ የተሰ
ጠችው ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ ምንድር ፡ ናት ? ። የእ
ግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡
እግዚአብሔርን ፡ የሚፈሩና ፡ ምእመናን ፡ በሚ
ሆኑ ፡ ሰዎች ፡ በሚመስሏቸውም ፡ እጅ ፡ የተ
ጠበቀ ፡ ይሁን ፡ ማለታቸው ፡ ነው ።

፰፻ ስድስተኛ ፡ ክፍል ። የትእዛዛት ፡ ፍጻሜ ፡ ግን ፡
አሥር ፡ ነው ። መጀመሪያ ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡
ከጎለቱለት ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ እንዳይወጣ ፡ እስኪ
ሞት ፡ ድረስ ፡ ከተሰጠው ፡ ሰጪ ፡ እንድስ ፡
እንኳ ፡ አይውጣ ፡ ከጉልቱም ፡ ምንም ፡ አይሸጥ
ቢሸጥም ፡ በአንቀጸ ፡ መጋቢ ፡ ምጽዋት ፡ እንደ
ተጻፈ ፡ ዋጋው ፡ ይመለስ ። (ፍ ፡ ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፯፻፷)
ሊሰጡት ፡ ሊቀበሉት ፡ ሊያስይዙት ፡ ሊይዙት ፡
ሊመጸውቱት ፡ አይገባም ። በርሱም ፡ በማይ
ገባ ፡ አይሥሩበት ።

፰፻፩ ሁለተኛም ፡ የውሳኔው ፡ ሥርዓት ፡ ለተጎለተ
ለት ፡ ሰው ፡ ይሁን ፡ ይኸውም ፡ የውሳኔው ፡
(የጉልቱ) ፡ ሥርዓት ፡ ነው ። የምጽዋትን ፡ ስጦ
ታ ፡ በሚናገር ፡ በአንቀጸ ፡ አብጥሊስ ፡ (ሲኖ
ዶስ) ፡ እንደ ተነገረ ፡ ይኸውም ፡ ከርሱ ፡ የዘወ
ትር ፡ ጥቅም ፡ የሚገኝበት ፡ የመጽሐፉ ፡ ሥር
ዓት ፡ የማይከለከል ፡ ነው ።

፰፻፪ ሦስተኛም ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡ ስሄደ ፡ ሰው ፡ ቢጎለ
ትለት ፡ የጕልቱን ፡ ሥርዓት ፡ ከመጻፋቸው ፡
አስቀድሞ ፡ መታጣቱ ፡ ቢታወቅ ፡ ለቤተ ፡ ክር
ስቲያን ፡ ይሁን ፡ ስለርሱ ፡ የታዘዘው ፡ ለተቸገ
ሩት ፡ ብቻ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ስለጉልትና ፡ ስለ
ሁለተኛው ፡ እንደ ተነገረ ።

አንቀጽ ፡ ፲፰ ።

፯፻፫ ወለእመ ፡ ሀለወ ፡ ፩ዱ ፡ እምእዝማዲሁ ፡ ለዘጐ ለቁ ፡ ሎቱ ፡ ወጽኑስ ፡ ውእቱ ፡ ይለዎ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ የሀብዎ ፡ እምኔሁ ፡ መጠነ ፡ መፍቅዱ ፡ ወእመ ፡ እኮሰ ፡ የሀብዎሙ ፡ ለጽኑሳነ ፡ ወያብ ድርዎሙ ፡ እምእዝማዲሁ ፡ ለዘጐለተ ። ወእ መሰ ፡ እልቦ ፡ እምውስቴቶሙ ፡ ጽኑስ ፡ ይኩ ውን ፡ ለጽኑሳን ፡ ለባሕቲቶሙ ፡ ለዘጽኑስ ፡ ፈድ ፋደ ፡ እምነ ፡ ጽኑስ ።

፯፻፬ ወከማሁ ፡ ለእመ ፡ ጐለቶ ፡ ለዘኢይደልዎ ፡ አው ፡ ለእመ ፡ ኢተወከፎ ፡ ዘጐለትዎ ፡ ሎቱ ፡ ይኩን ፡ ለዘይደልዎ ፡ እምነ ፡ ዘኢይደልዎ ። ወእመኒ ፡ ጐለቶ ፡ ለዘይደልዎ ፡ ወለዘኢይደ ልዎ ፡ ይኩን ፡ ዘቀዳሚ ፡ ወያግብእ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘኢይደሉ ፡ በከመ ፡ ተሠርዐ ። ወለእመ ፡ ተአዘዘ ፡ ዘይደልዎ ፡ ወዘኢይደልዎ ፡ ይጽናዕ ፡ ዘይደሉ ፡ ወያብጥሉ ፡ ዘኢይደሉ ።

፯፻፭ ወለእመ ፡ ተወሰነ ፡ ፍጻሜሁ ፡ ዘጊዜ ፡ እሙር ፡ ለይኩን ፡ ወይትገበር ፡ እምድኅሬሁ ፡ በከመ ተሠርዐ ለዘይደልዎ ። ወለእመ ፡ ኮነ ዘጐ ለቁ ፡ ሎቱ ፡ ጽኑስ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይንሣእ ፡ እምተጋብኦቱ ፡ ለመፍቅዱ ፡ ዚእሁ ፡ ወከማሁ ሶበ ሞተ ፡ እቀሚሁ ፡ ለውእቱ ።

፯፻፮ ራብዕ ፡ ከመ ፡ ይሥራዕ ፡ ጐላቲ ፡ እመንገለ ፡ ፍና ፡ ዘእዘዘ ፡ ባቲ ፡ ዘጐለቶ ፡ ወለእመ ፡ ኢእ ዘዘ ፡ ምንተኒ ፡ እምኵሉ ፡ ዘይትጋባእ ፡ እም ኔሁ ፡ ትእዛዘ ፡ ጐላቲ ፡ በዝንቱ ፡ እው ፡ ሶበ ፡ ኢእዘዘ ፡ እመኒ ፡ ሠምረ ፡ ቦቱ ፡ ዘጐለቱ ፡ ላዕ ሌሁ ፡ እው ፡ እመ ፡ ኢሠምረ ፡ ቦቱ ።

፯፻፯ ወኃምስ ፡ ወለእመ ፡ ተንሥተ ፡ እምኔሁ ፡ ግብር፡ ዘይደልዎ ፡ በቍዔት ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይሕን ጽዎ ፡ እመኒ ፡ በውእቱ ፡ ጊዜ ፡ አው ፡ እምድኅ ሬሁ ።

፯፻፰ ወሳድስ ፡ ወእመኒ ፡ ኮነ ፡ ነዳየ ፡ ዝንቱ ፡ ዘጐ ለቶ ፡ ላዕለ ፡ ጽኑሳን ፡ ለባሕቲቶሙ ፡ ሎቱ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ የሀብዎ ፡ እምዘተጋብእ ፡ በእ ንተ ፡ ዓጸባሁ ።

፯፻፱ ወሳብዕኒ ፡ ወለእመ ፡ ቦቱ ፡ ለብእሲ ፡ መክፈ ልት ፡ ውስተ ፡ ንዋይ ፡ ዘዕዉቅ ፡ ይከውኖ ፡ ከመ ፡ ይጐልቶ ፡ ወለእመ ፡ መጽአ ፡ እምድኅረ፡ ዝንቱ ፡ ስታፌሁ ፡ በውስተ ፡ ከፍል ፡ ይከውኖ፡ እንከ ፡ ከመ ፡ ይትከፈል ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ እምነ ፡ ዘይትከሀል ፡ ተከፍሎቱ ።

፯፻፲ ወሳምንሂ ፡ ወኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ በላዕ

ስለ ፡ ዘሥራት ።

፯፻፫ ከጐለቱለት ፡ ሰው ፡ ዘመዶች ፡ ወገን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ችግረኛም ፡ ቢሆን ፡ ከጉልቱ ፡ የሚሻውን ፡ ያህል ፡ ሊሰጡት ፡ ይገባዋል ። ይህም ፡ ባይሆን ፡ ለተቸገሩት ፡ ሰዎች ፡ ይሰጧ ቸው ፡ ከጐለተው ፡ ሰው ፡ ዘመዶች ፡ ወገንም ፡ አብልጠው ፡ ይስጧቸው ። ከርሱ ፡ ወገን ፡ ችግ ረኛ ፡ ባይኖር ፡ ግን ፡ ለተቸገሩት ፡ ብቻ ፡ ይሁን። ይልቁንም ፡ ከተቸገረው ፡ ፈጽሞ ፡ ለተቸገረው።

፯፻፬ እንደዚሁም ፡ ለማይገባው ፡ ቢጐልተው ፡ ወይም ፡ የጐለቱለት ፡ ሰው ፡ ባይቀበለው ፡ ከማ ይገባው ፡ ይልቅ ፡ ለሚገባው ፡ ይሁን ። ለሚገ ባውና ፡ ለማይገባው ፡ ቢጐለትለት ፡ ለመጀ መሪያው ፡ ይጽናለት ። ለማይገባው ፡ ቢጐለት ለት ፡ ግን ፡ እንደታዘዘ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይሁን ። የሚገባና ፡ የማይገባ ፡ ቢታዘዝ ፡ የሚገ ባው ፡ ይጽና ፡ የማይገባውንም ፡ ያፍርሱ ።

፯፻፭ በታወቀ ፡ ጊዜ ፡ ፍጻሜው ፡ ቢወሰን ፡ ለሚገ ባው ፡ እንደታዘዘ ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ ፈጽሞ ፡ ይሁን ። የጐለቱለት ፡ ሰው ፡ ችግረኛ ፡ ቢሆን ፡ እርሱ ፡ የሚፈልገውን ፡ ከተሰበሰበው ፡ መው ሰድ ፡ ይገባዋል ፡ ለርሱም ፡ ጐላቹ ፡ ቢሞት ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ።

፯፻፮ አራተኛ ፡ የጐለተው ፡ ሰው ፡ ከአዘዘባት ፡ ሥራ፡ ወገን ፡ ጐላት ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ። ጐላ ቹ ፡ ከጉልቱ ፡ ከሚሰበሰበው ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ምንም ፡ ባያዝዝ ፡ ወይም ፡ ባላዘዘ ፡ ጊዜ ፡ የጐለ ቱለት ፡ ሰው ፡ ቢወድ ፡ ወይም ፡ ባይወድ ።

፯፻፯ አምስተኛ ፡ ከርሱ ፡ ወገን ፡ ጥቅም ፡ ያለበት ፡ ሥራ ፡ ቢፈርስ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ ቢሆንም ፡ ሊያድሱት ፡ ይገባል ።

፯፻፰ ስድስተኛ ፡ ለተቸገሩት ፡ ብቻ ፡ የጐለተው ፡ ሰው ፡ ድኻ ፡ ቢሆን ፡ ስለችግሩ ፡ ከተሰበሰበው ፡ ሊሰጡት ፡ ይገባዋል ።

፯፻፱ ሰባተኛም ፡ የታወቀ ፡ የገንዘብ ፡ ድርሻ ፡ ያለው፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ሊጐልተው ፡ ይገባዋል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ለመካፈል ፡ ባልንጀራው ፡ ቢመጣ ፡ መክፈል ፡ የሚቻል ፡ ከሆነ ፡ እንዲህ ፡ መክፈል፡ ይገባዋል ።

፯፻፲ ስምንተኛም ፡ ባስልዮስ ፡ እንደተናገረ ፡ የነ

ሲሁ ፡ ጸባሕተ ፡ ንጉሥ ፡ በከመ ፡ ዘከረ ፡ ባስል
ዮስ ።

፯፻፲፩ ወታስዕኒ ፡ ወኢይጸንዕ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘተእምኖ ፡ በቅድሜሆሙ ፡ ለእለ ፡ ይከውኑ ፡ ሰምዐ ። ወቃላተ ፡ ነገሩስ ፡ ዘይብል ፡ እነ ፡ አቀምኩ ፡ አው ፡ በሃዕኩ ፡ አው ፡ ጐለትኩ ፡ ዘከመ ፡ ማኅደረ ፡ ነግድ ፡ ወዘከመ ፡ በዘቅት ። ወሰማዕትኒ ፡ እለ ፡ ይጸንዑ ፡ ስምዖሙ ፡ በውስተ ፡ መጽሐፉ ፡ እንተ ፡ ተጽሕፈት ፡ ይኩኑ ፡ ሰጢቃነ ፡ በኒሩት ፡ ወበ አእምሮ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ መካን ። ወኊልቆሙሰ ይኩን ፡ ፯ተ ፡ አው ፡ ፭ተ ፡ በከመ ፡ ነገሩ ፡ አብጥሊሳት ፡ በእንተ ፡ መጽሐፈ ፡ ትእዛዝ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ በውስተ ፡ መካን ፡ ዘኢይትረከብ ፡ ውስቴቱ ፡ ፯ቱ ፡ ወኢ ፡ ፭ቱ ፡ ይኩኑ ፡ ፪ቱ ፡ አው ፡ ፫ቱ ፡ እምነ ፡ ኄራኒሆሙ ፡ ለእለ ፡ ሀለዉ ፡ ህየ ።

፯፻፲፪ ዓሥር ፡ ወኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኅብአ ፡ ኪያሁ ፡ ኢ ፡ ዘጐለቱ ፡ ሎቱ ፡ ኢ ፡ ለካልኡ ፡ ኢ ፡ ኵሎን ቃሁ ፡ ወኢመንፈቀ ፡ ዚአሁ ፡ ከመ ፡ ይብልዑ ፡ ድኅረ ፡ ወይፍርሁ ፡ እምዘተገብረ ፡ በአምሳለ ፡ ዝንቱ ፡ ላዕለ ፡ ሐናንያ ፡ ወብእሲቱ ፡ እለ ፡ አገ ቶሙ ፡ ሞተ ፡ መዓት ፡ እመ ፡ ሣጥዋ ፡ ለዓፀ ያሙ ፡ እንተ ፡ አሕረምዋ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወተሰነዐወ ፡ ምስለ ፡ ብእሲቱ ፡ ከመ ፡ ይኅብኡ፡ መንፈቀ ፡ ሤጡ ። በከመ ፡ ስምዐ ፡ ኮነ ፡ መጽ ሐፈ ፡ አብርክሲስ ፡ ወዓዲ ፡ ዘከመ ፡ ሣቀዮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአካን ፡ ወልደ ፡ ከርሚ ፡ ሶበ ፡ ኀብአ ፡ ንዋየ ፡ ዘንሥአ ፡ እምሰብአ ፡ ኢያሪኮ ፡ ዘረሰዮ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፡ ቅዱሰ ፡ ለእግዚ አብሔር ፡ እስከ ፡ ዐደወ ፡ ኰነኔሁ ፡ በዝንቱ ፡ ላዕለ ፡ ውሉዱ ፡ ወእንስሳሁ ።



ጉሥ ፡ ግብር ፡ ሊኖርበት ፡ አይገባም ።

፯፻፲፩ ዘጠኝኛም ፡ ምስክር ፡ በሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ፊት ፡ ቢታመን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አይጸናም ። የሚናገ ረው ፡ የነገሩ ፡ ቃላት ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ወሰንኩ ፡ ወይም ፡ ተሳልኩ ፡ ወይም ፡ ጐለትኩ ፡ ይኸ ውም ፡ እንደ ፡ እንግዳ ፡ ማደሪያ ፡ እንደ ፡ ውኃ ፡ ጕድጓድ ፡ ያለውን ፡ ነው ። ምስክርነታቸው ፡ በተጻፈችው ፡ ደብዳቤ ፡ የሚጸና ፡ ምስክሮችም ፡ በቦታው ፡ ሁሉ ፡ በቸርነትና ፡ በእውቀት ፡ የታ ወቁ ፡ ይሁኑ ። ቍጥራቸው ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ትእ ዛዝ ፡ መጽሐፍ ፡ አብጥሊሳት ፡ እንደተናገሩ ፡ ፯ ፡ ወይም ፡ አምስት ፡ ይሁን ። ፯ት ፡ ይህም ፡ ባይሆን ፡ ፭ት ፡ የማይገኙበት ፡ ቦታ ፡ ቢሆን ፡ ከዚያ ፡ ካሉት ፡ ከደጋጉ ፡ ወገን ፡ ሁለት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ ይሁኑ ።

፯፻፲፪ አሥረኛ ፡ ጉልቱን ፡ መሰወር ፡ አይገባም ፡ የጐ ለቱለትም ፡ ቢሆን ፡ ባልንጀራውም ፡ ቢሆን ፡ መላውም ፡ እኩሌታውም ፡ ቢሆን ፡ ኋላ ፡ ይመ ገቡት ፡ ዘንድ ፡ በዚህ ፡ አምሳል ፡ የቁጣ ፡ ሞት ፡ ባገኛቸው ፡ በሐናንያና ፡ በሚስቱ ፡ ላይ ፡ ከተደ ረገው ፡ የተነሣ ፡ ይፍሩ ። ለእግዚአብሔር ፡ የሰ ጧትን ፡ ቦታቸውን ፡ በሸጡ ፡ ጊዜ ፡ የሐዋርያት ሥራ ፡ እንደመሰከረ ፡ የዋጋውን ፡ እኩሌታ ፡ ይሸሽጉ ፡ ዘንድ ፡ ከሚስቱ ፡ ጋር ፡ ተስማማ ። (የሐዋ ፡ ፭ ፡ ፩-፲፩) ። ዳግመኛም ፡ የነዌ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተለየ ፡ ያደረገውን ፡ ከኢያሪኮ ፡ ሰዎች ፡ የማረከውን ፡ ገንዘብ ፡ በሸ ሸገ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ የከርሚ ልጅ ፡ አካ ንን ፡ ቀሰፈው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ቅጣቱ ፡ በልጆቹና ፡ በከብቶቹ ፡ ላይ ፡ እስካለፈ ፡ ድረስ ። (ኢያሱ ፡ ፯ ፡ ፲፰ - ፳፮) ።

## አንቀጽ ፡ ፲ወ፱ቱ ።

በእንተ ፡ ዕለተ ፡ እሑድ ፡ ወዕለተ ፡ ሰንበት ፡ ወበ ዓላተ ፡ እግዚእ ፡ ወምክንያተ ፡ አብዕሎቶሙ ።

፯፻፲፫ ዶቅ ፡ ጽወ፱ቱ ፡ ኢይደልዎሙ ፡ ለክርስቲያን ፡ ከመ ፡ ያዕርፉ ፡ ተገብሮ ፡ በዕለተ ፡ ሰንበት ፡ ከመ ፡ አይሁድ ፡ አላ ፡ ይትገበሩ ፡ በውእቱ ፡ ዕለት ፡ ከመ ፡ ክርስቲያን ። ወለእመ ፡ ተረከቡ ፡

## አንቀጽ ፡ ፲፱ ።

ስለ ፡ ዕለተ ፡ እሑድ ፡ ስለ ፡ ዕለተ ፡ ቀዳሚት ፡ ስለ ፡ ጌታ ፡ በዓላት ፡ ስለሚከበሩበትም ፡ ምክን ያት ።

፯፻፲፫ ዶቅ ፡ ጽ፱ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደ ፡ አይሁድ ፡ በዕ ለተ ፡ ቀዳሚት ፡ ተግባርን ፡ ማጕደል ፡ አይገባ ቸውም ፡ በዚያች ፡ ዕለት ፡ እንደ ፡ ክርስቲያን ፡ ይሥሩ ፡ እንጂ ። ከሕዝቡ ፡ ወገን ፡ የአይሁድን፡

እምሕዝብ ፡ እንዘ ፡ ይገብሩ ፡ ግብረ ፡ አይሁድ ፡ ውእቶሙ ፡ ይክውኑ ፡ ስዱዳነ ፡ እምቅድመ ፡ ገጹ ፡ ለክርስቶስ ።

፯፻፲፩ ዘኒቅያ ፡ ፳ ፡ ወኢትትዓቀቡ ፡ ሰንበተ ፡ ከመ ፡ አይሁድ ።

፯፻፲፪ መክ ፡ ወኢይኩን ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ ወበዓላት ፡ ክቡራን ፡ ሰጊድ ፡ አስመ ፡ እሉ ፡ መዋዕለ ፡ ፍሥሓ ፡ ውእቶሙ ፡ ወበእንተዝ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ናፅርዕ ፡ ገቢረ ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ ወበበዓላት ፡ ወዝንቱ ፡ አንቀጽ ፡ ዘእንበለ ፡ ግዘት ።

፯፻፲፫ መክ ፡ ዘ፵ ፡ ወያአትቱ ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ እም ኵሎሙ ፡ ምእመናን ፡ አቅሞተ ፡ ውሳኔያት ፡ ሥልጣናውያት ፡ ዘፍትሕ ፡ ወኢያግበሩ ፡ ቅስተ ፡ ወተኳንኖ ፡ ወኢያኅሥሥ ፡ እምኔሁ ፡ በይእቲ ፡ ዕለት ፡ ንዋዮ ፡ እምካልኡ ፡ ወኢያጽ ሐቅ ፡ ፩ዱሂ ፡ እምእመናን ፡ በእንተ ፡ ኀሢሠ ፡ ዕዳ ፡ አው ፡ ተጸልአ ፡ አው ፡ ዘይመስሎ ፡ ለዝ ንቱ ።

፯፻፲፬ ወይሑሩ ፡ ቦቱ ፡ ኵሎሙ ፡ ሰብእ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወይምጽኡ ፡ ኵሉ ፡ ለለ፩ዱ ፡ እም እመናን ፡ ኀቤሃ ፡ በንጽሕ ፡ ወበትሕትና ፡ ዘእን በለ ፡ ፍርሃት ፡ እምነ ፡ መኰንን ፡ ወእምበዓለ ፡ ዕዳ ፡ አው ፡ እምፈታሒ ፡ ወዘይመስሎ ፡ ለዝ ንቱ ። ወእመሰ ፡ ተኀበለ ፡ ፩ዱ ፡ አመጸብሐን ፡ ከመ ፡ ይንሣእ ፡ ጸባሕተ ፡ እምእለ ፡ የሐውሩ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይፍዲ ፡ ምክዕቢተ ።

፯፻፲፭ ድስቅ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ተጋብኡ ፡ ኵሎ ፡ ዕለተ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወፈድፋደሰ ፡ በዕለተ ፡ ሰን በት ፡ ወበዕለተ ፡ ትንሣኤ ፡ ዘውእቱ ፡ ዕለተ ፡ እሑድ ። ወናሁ ፡ ንሬእዮሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ከመ ፡ ኢይዴኀሩ ፡ እምተጋብኦ ፡ በዕለተ ፡ በዓሎሙ ፡ አላ ፡ ይፀመዱ ፡ ኵሎሙ ፡ በውእቱ ፡ ዕለት ፡ ወከማሁ ፡ ጉባኤ ፡ አይሁድ ፡ እለ ፡ ይሰመዩ ፡ በከንቱ ፡ አይሁደ ፡ ያፀርዑ ፡ ተግባሮሙ ፡ እም ድኅረ ፡ ሰዱስ ፡ መዋዕል ፡ ወይትጋብኡ ፡ በዕ ለት ፡ ሳብዕት ፡ ውስተ ፡ ምኵራቦሙ ፡ ወያፀርዑ ተግባሮሙ ፡ ዘተሠርዐ ፡ ሎሙ ፡ አመ ፡ ተጋብ ኦቶሙ ። ወእመሰኬ ፡ ኮኑ ፡ እሉ ፡ ትጉሃነ ፡ በእ ንተ ፡ ተጋብኦቶሙ ፡ ዕሩዕ ፡ ዘእልቦ ፡ ረባኀ ፡ ሎሙ ፡ ወምንተኬ ፡ እንተ ፡ ታወሥእ ፡ ለእግዚ አብሔር ፡ ዘትዴኀር ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያኑ ።

፯፻፲፮ ሸወ፮ቱ ፡ ወኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ትትናገሩ ፡ ነገረ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ረባኀ ፡ አው ፡ ትግበሩ ፡ ግብረ ፡ ዘኢ



ሥራ ፡ ሲሠሩ ፡ ቢገኙ ፡ እነርሱ ፡ ከክርስቶስ ፡ ፊት ፡ የተለዩ ፡ ይሆናሉ ።

፯፻፲፩ ኒቅያ ፡ ፳ ፡ እንደ ፡ አይሁድ ፡ ቀዳሚትን ፡ አት ጠናቀቁ ።

፯፻፲፪ መክ ፡ በእሑድና ፡ በተከበሩት ፡ በዓላት ፡ ቀን ፡ ሰግደት ፡ አይገባም ፡ እነዚህ ፡ የደስታ ፡ ቀኖች ናቸውና ። ስለዚህ ፡ በእሑድና ፡ በበዓላት ፡ ቀን፡ ሥራ ፡ መፍታት ፡ ይገባል ፡ ይህ ፡ ያልተወገዘ በት ፡ አንቀጽ ፡ ነው ።

፯፻፲፫ መክ ፡ ፵ ፡ የፍርድ ፡ ዳኞች ፡ የተወሰነውን ፡ ሥር ዓት ፡ ከምእመናን ፡ ሁሉ ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ ያርቁ ፡ ክርክርን ፡ ፍርድን ፡ አያድርጉ ። እርሱ ም ፡ በዚች ፡ ዕለት ፡ ከባለዕዳው ፡ ገንዘቡን ፡ አይ ፈልግ ። ከምእመናን ፡ ወገን ፡ አንዱስ ፡ እንኳ ፡ ገንዘቡን ፡ ለመፈለግ ፡ ወይም ፡ ለመጣላት ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ ለሚመስለው ፡ አይትጋ ።

፯፻፲፬ ሰዎቹ ፡ ሁሉ ፡ ወደቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይሂዱ በት ። ከምእመናን ፡ ወገን ፡ ሁሉም ፡ ለእያን ዳንዱ ፡ ወደርሱ ፡ በንጽሕና ፡ በትሕትና ፡ ይም ጡ ፡ ገዢውን ፡ አበዳሪውን ፡ ዳኛውን ፡ ይህ ንም ፡ የመሰለውን ፡ ያለመፍራት ። ከእስገባሪ ዎች ፡ ወገን ፡ አንዱ ፡ ወደቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሚሄዱት ፡ ሰዎች ፡ ግብር ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ ቢደፋፈር ፡ ግን ፡ እጥፍ ፡ ድርብ ፡ ይክፈል ።

፯፻፲፭ ድስቅ ፡ ፲፪ ፡ ዘወትር ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተሰ ብሰቡ ። ይልቁንም ፡ በዕለተ ፡ እሑድና ፡ በዕለተ ትንሣኤ ፡ ይኸውም ፡ ዕለተ ፡ እሑድ ፡ ነው ። እነሆ ፡ በበዓላቸው ፡ ቀን ፡ ከመሰብሰብ ፡ ወደ ኋላ ፡ እንደማይሉ ፡ አሕዛብን ፡ እናያቸዋለን ። በበዓሉ ፡ ቀን ፡ ሁሉም ፡ ይሰበሰባሉ ፡ እንጂ ፤ እንደዚሁም ፡ በከንቱ ፡ አይሁድ ፡ የሚባሉ ፡ የተ ሰበሰቡ ፡ አይሁድ ፡ ከስድስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ሥራቸውን ፡ ይተዋሉ ። በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ በምኵራባቸው ፡ ይሰበሰባሉ ፡ በተሰበሰቡም ፡ ጊዜ ፡ የታዘዘላቸውን ፡ ሥራቸውን ፡ ይተዋሉ ። እነዚህ ፡ ጥቅም ፡ ለሌለበት ፡ ለማይረባ ፡ መሰ ብሰባቸው ፡ የሚተጉ ፡ ከሆኑ ፡ ግን ፡ ከቤተ ፡ ክር ስቲያን ፡ ወደኋላ ፡ የምትል ፡ አንተ ፡ ለእግዚ አብሔር ፡ የምትመልስለት ፡ ምንድር ፡ ነው ? ።

፯፻፲፮ ሸ፮ ፡ ጥቅም ፡ የሌለበትን ፡ ነገር ፡ ትናገሩ ፡ ዘንድ ፡ ወይም ፡ መልካም ፡ ያይደለውን ፡ ሥራ ፡

ይሜኒ ፡ ወፈድፋደሰ ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ትትፈሥሑ ፡ ፍሥሓ ፡ መንፈሳዊተ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ዳዊት ፡ ነቢይ ፡ "ተቀነዩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በፍርሃት ፡ ወተኃሠዩ ፡ ሎቱ ፡ በረዓድ" ።

፩፻፹ ሥርዋጽ ፡ ያኤምር ፡ ኀበ ፡ ቃለ ፡ ዳዊት ፡ ዘይቤ ፡ "ዛቲ ፡ ዕለት ፡ እንተ ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንትፈሣሕ ፡ ወንትኀሠይ ፡ ባቲ ።

፩፻፹፩ ረስጣ ፡ ፳ወ፮ቱ ፡ ወእግብርትኒ ፡ ይትቀነዩ ፡ ሐምስ ፡ መዋዕለ ፡ ወበዕለተ ፡ ሰንበትሰ ፡ ወእሑድ ፡ ይፀመዱ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከመ ፡ ይትመሀሩ ፡ መልእክተ ፡ እግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ በዕለተ ፡ ሰንበት ፡ አዕረፈ ፡ እግዚአብሔር ፡ እመ ፡ ፈጸመ ፡ ፈጢረ ፡ ፍጥረታት ፡ ወበዕለተ ፡ እሑድኒ ፡ ተንሥአ ፡ እምነ ፡ ምውታን ።

፩፻፹፪ ድስቅ ፡ ፴ወ፩ዱ ፡ ወበኵሉ ፡ ዕለተ ፡ ሰንበት ፡ ዘእንበለ ፡ ዕለተ ፡ ፍሥሕ ፡ ባሕቲቱ ፡ ወበኵሉ ፡ ዕለተ ፡ እሑድ ፡ ተመጠዉ ፡ ቍርባነ ፡ በበይናቲከሙ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወተፈሥሑ ።

፩፻፹፫ ወናሁ ፡ ተነግረ ፡ በአንቀጸ ፡ ጾም ፡ ከመ ፡ ኢይጹሙ ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ ወሰንበት ፡ ዘእንበለ ፡ ሰንበት ፡ ዘኮነ ፡ ባቲ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ቅቡረ ፡ ውስተ ፡ መቃብር ።

፩፻፹፬ ወናሁ ፡ ነገሩ ፡ በጉባኤ ፡ ፫፻፲ወ፰ቱ ፡ በጽድቀ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘይደሉ ፡ በእንተ ፡ በዓላት ፡ ዘእግዚእነ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ እንዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስሌሆሙ ፡ ከመ ፡ ይዕቀቡ ፡ በዓላተ ፡ እግዚእነ ፡ ወይሰብሑ ፡ ተአምራቲሁ ፡ ወቅዳሴያቲሁ ። እሉ ፡ እሙንቱ ፡ በዓለ ፡ ልደት ፡ ወበዓለ ፡ ጥምቀት ፡ ወበዓለ ፡ ሆሣዕና ፡ ወኵሉ ፡ በዓላተ ፡ ትስብእት ፡ ዘፈጸማ ፡ ትንሣኤሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ እማእከለ ፡ ሙታን ፡ ወበዓለ ፡ ዕርገት ፡ ወበዓለ ፶ ፡ ዘውእቱ ፡ ርደቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ ዘከመ ፡ አሰፈዎሙ ፡ እግዚእነ ፡ ለአርዳኢሁ ፡ ወበዓለ ፡ ታቦር ፡ ወቦቱ ፡ ተወለጠ ወአእመሩ ፡ አርዳኢሁ ፡ ስብሐተ መለኮቱ ። ወእሉ ፡ ፯ቱ ፡ በዓላት ፡ ክቡራን ፡ ወዝንቱ ፡ ቃል ፡ ዘተነግረ ፡ ለጉባኤ ፡ በከመ ፡ ተረክበ ፡ በዲድስቅልያ ።



ትሠሩ ፡ ዘንድ ፡ አይገባም ፡ ይልቁንም ፡ መንፈሳዊ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ልታደርጉባት ፡ በምትገባ ፡ ዕለተ ፡ እሑድ ፡ ነቢዩ ፡ ዳዊት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በፍርሐት ፡ ተገዙ ፡ በመንቀጥቀጥም ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ፡ ብሎ ፡ እንደተናገረ ። (መዝ ፡ ፪ ፡ ፲፩) ።

፩፻፹ ሥርዋጽ ፡ ፈጽመን ፡ ደስ ፡ እንሰኝባት ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ የፈጠራት ፡ (ያከበራት) ፡ ቀን ፡ ይህች ፡ ናት ፡ ብሎ ፡ ወደተናገረው ፡ ወደዳዊት ፡ ቃል ፡ ያመለክታል ። (መዝ ፡ ፻፲፯ ፡ ፳፬) ።

፩፻፹፩ ረስጣ ፡ ፳፪ ፡ አገልጋዮችም ፡ አምስት ፡ ቀን ፡ ያገልግሉ ፡ ቅዳሜና ፡ እሑድ ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ አገልግሎት ፡ ይማሩ ፡ ዘንድ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይዋሉ ። በዕለተ ፡ ቀዳሚት ፡ ፍጥረታትን ፡ ፈጥሮ ፡ በጨረሰ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ አርፎባታልና ፡ በዕለተ ፡ እሑድም ፡ ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ ተነሥቶባታልና ።

፩፻፹፪ ድስቅ ፡ ፴፩ ፡ ከዕለተ ፡ ፍሥሕ ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ በዕለተ ፡ ቀዳሚትና ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ ሁሉ ፡ እያንዳንዳችሁ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ተቀበሉ ፡ ደስም ፡ ይበላችሁ ።

፩፻፹፫ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በመቃብር ፡ ተቀብሮ ፡ ካደረባት ፡ ቅዳሜ ፡ በቀር ፡ እሑድና ፡ ቅዳሜ ፡ እንዳይጾሙ ፡ እነሆ ፡ በአንቀጸ ፡ ጾም ፡ ተነገረ ። (ፍ ፡ ነገ ፡ ፲፭ ፡ ፭፻፸፯) ።

፩፻፹፬ እግዚአብሔር ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ስለሆነ ፡ ፫፻፲፰ ሊቃውንት ፡ ስለጌታችን ፡ በዓላት ፡ የሚገባውን በእግዚአብሔር ፡ አጋዥነት ፡ በአንድነት ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ እነሆ ፡ ተናገሩ ። የጌታችንን ፡ በዓላት ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ተአምራቱንና ፡ ምስጋናውንም ፡ ይገልጡ ፡ ዘንድ ። እነዚህም ፡ የልደት ፡ የጥምቀት ፡ የሆሣዕና ፡ በዓልና ፡ ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ የጌታችን ፡ መነሣት ፡ (ትንሣኤ) የተፈጸመባት ፡ የትስብእት ፡ በዓላት ፡ ሁሉ ፡ ናቸው ። በዓለ ፡ ዕርገት ፡ በዓለ ፶ ፡ ይኸውም ፡ ጌታችን ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ተስፋ ፡ እንደነገራቸው ፡ አጽናኝ ፡ የሚሆን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የወረደበት ፡ ነው ። ራእዩ ፡ የተለወጠበትና ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ባሕርየ ፡ መለኮቱን ፡ ያወቁበት ፡ በዓለ ፡ ደብረ ፡ ታቦርም ፡ ነው ። እነዚህም ፡ ፯ ፡ በዓላት ፡ የከበሩ ፡ ናቸው ።

፯፻፳፭ ወጥንተ ፡ በዓላትኒ ፡ ልደት ፡ ውእቱ ፡ ወቦ ፡ ዘይቤ ፡ በዓለ ፡ ትስብእት ፡ ጥንተ ፡ በዓላት ፡ ወኢንሬኢ ፡ በዝንቱ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ እምዘ ሎሙ ፡ በዓላተ ፡ እግዚእን ፡ ዐቢያት ፡ ወለእግ ዚአብሔር ፡ አኰቴት ። ወጥንተ ፡ በዓለ ፡ እግዚ ዚአ ፡ በዓለ ፡ ብሥራት ፡ እምእግዚአብሔር ፡ ስቡሕ ፡ በልሳነ ፡ ገብርኤል ፡ መልአክ ፡ ዘነገሩ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ድንግል ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ መድኃኒነ ፡ አመ ፡ ፳ወ፱ሁ ፡ ለወርኀ ፡ መጋቢት ።

፯፻፳፮ ድስቅ ፡ ፳ወ፱ቱ ፡ አ ፡ አኃውየ ፡ ተዐቀቡ ፡ በዕ ለተ ፡ በዓላት ፡ ዘውእቱ ፡ በዓለ ፡ ልደቱ ፡ ለእግ ዚእን ፡ ወግበሩ ፡ አመ ፡ ፳ወ፭ሱ ፡ ለታስዕ ፡ ወርኀ ፡ ዘዕብራውያን ፡ ዘውእቱ ፡ አመ ፡ ፳ወ ፱ሁ ፡ ለራብዕ ፡ ወርኀ ፡ ዘግብጻውያን ። ወእም ድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ግበሩ ፡ በዓለ ፡ ኤጲፋንያ ፡ ዘው እቱ ፡ በዓለ ፡ ጥምቀት ፡ ወይኩን ፡ በኀቤክሙ ፡ ክቡረ ፡ እስመ ፡ ቦቱ ፡ ወጠነ ፡ እግዚእን ፡ ከመ ፡ ያርኢ ፡ መለኮቶ ፡ አመ ፡ ተጠምቀ ፡ በውስተ ፡ ዮርዳኖስ ፡ በእደ ፡ ዮሐንስ ። ወግበሩ ፡ አመ ፡ ፳ኡ ፡ ለዓሥር ፡ ወርኀ ፡ ዘዕብራውያን ፡ ዘው እቱ ፡ አመ፲ወ፩ ፡ ለኃምስ ፡ ወርኀ ፡ ዘምስራ ውያን ።

፯፻፳፯ በስ ፡ ፴ ፡ ወይኩን ፡ ገቢረ ፡ ቍርባን ፡ በልደት ፡ ወጥምቀት ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ እስ ፡ ለጸ ሊእ ፡ ጾም ፡ እላ ፡ በእንተ ፡ ክብረ ፡ በዓል ።

፯፻፳፰ ግንር ፡ ፲ወ፩ዱ ፡ ወያብዕሉ ፡ በዓለ ፡ ሆሣዕና ።

፯፻፳፱ ድስቅ ፡ ፴ ፡ ያደልወክሙ ፡ አ ፡ አኀውየ ፡ ዘተ ሣየጠክሙ ፡ በደሙ ፡ ክቡር ፡ ዘውእቱ ፡ ደመ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከመ ፡ ትግበሩ ፡ በዓለ ፡ ፋሲካ ፡ በኵሉ ፡ ጻሕቅ ፡ ወእስተሐምሞ ፡ ዐቢይ ፡ እምድኅረ ፡ በሊዐ ፡ ናእት ፡ ወኢትግ በሩ ፡ ዘንተ ፡ በዓለ ፡ ተዝካረ ፡ ሕማሙ ፡ ለዋ ሕድ ፡ ፪ተ ፡ ጊዜ ፡ በ፩ዱ ፡ ዓመት ፡ አላ ፡ ፩ደ ፡ ጊዜ ፡ በእንተ ፡ ዘሞተ ፡ በእንቲአነ ፡ ፩ደ ፡ ጊዜ ።

፯፻፴ ወተዐቀቡ ፡ በተጠናቅቆ ፡ ብዙኀ ፡ እምበዓለ ፡ አይሁድ ፡ ዘውእቱ ፡ በሊዐ ፡ ናእት ፡ ዘይከውን ፡



ይኸውም ፡ ቃል ፡ በዲድስቅልያ ፡ እንደተገኘ ፡ በጉባኤ ፡ የተነገረው ፡ ነው ።

፯፻፳፭ የበዓላትም ፡ ጥንት ፡ (በዙር) ፡ ልደት ፡ ነው ፡ የበዓላት ፡ ጥንት ፡ (በዙር) ፡ በዓለ ፡ ትስብእት ፡ ነው ፡ የሚልም ፡ አለ ። ከታላላቁ ፡ ከጌታችን ፡ በዓላት ፡ ሁሉ ፡ እርሱ ፡ ጥንት ፡ እንደሆነ ፡ በዚህ ፡ እናይም ። ለእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ምስ ጋና ፡ ይግባውና ፡ የጌታ ፡ በዓል ፡ ጥንት ፡ አምላ ካችንን ፡ መድኃኒታችንን ፡ ለወለደች ፡ ለእመ ቤታችን ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ በመጋቢት ፡ ወር ፡ በ፳፱ ፡ ቀን ፡ ካእግዚአብሔር ፡ ታዝዞ ፡ በነገራት ፡ በመልአኩ ፡ በገብርኤል ፡ እንደ በት ፡ የተመሰገነ ፡ (የተነገረ) ፡ በዓለ ፡ ብሥራት ፡ ነው ፡

፯፻፳፮ ድስቅ ፡ ፳፱ ፡ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡ በበዓላት ፡ ቀን ፡ ተጠበቁ ፡ ይኸውም ፡ የጌታችን ፡ በዓለ ፡ ልደት ፡ ነው ። በዕብራውያን ፡ በዘጠኘኛው ፡ ወር ፡ በ፳፭ኛው ፡ ቀን ፡ አድርጉ ፡ ይኸውም ፡ በግብጻውያን ፡ በአራተኛው ፡ ወር ፡ በ፳፱ኛው ፡ ቀን ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በዓለ ፡ ኤጲፋንያን ፡ አድርጉ ፡ ይኸውም ፡ በዓለ ፡ ጥምቀት ፡ ነው ። በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ የከበረ ፡ ይሁን ። ጌታችን ፡ ጌትነቱን ፡ ያሳይ ፡ ዘንድ ፡ የጀመረበት ፡ ነውና ፡ በዮርዳኖስ ፡ በዮሐንስ ፡ እጅ ፡ በተጠመቀ ፡ ጊዜ ፡ በዕብራውያን ፡ በአሥረኛው ፡ ወር ፡ በ፳ ኛው ፡ ቀን ፡ አድርጉ ፡ ይኸውም ፡ በግብጻው ያን ፡ በአምስተኛው ፡ ወር ፡ በ፲፩ኛው ፡ ቀን ፡ ነው ።

፯፻፳፯ በስ ፡ ፴ ፡ በልደትና ፡ በጥምቀት ፡ ቅዳሴው ፡ በመንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ ይሁን ፡ ጾሙን ፡ በመጥ ላት ፡ አይደለም ፡ ስለበዓሉ ፡ ክብር ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፯፻፳፰ ግንር ፡ ፲፩ ፡ በዓለ ፡ ሆሣዕናን ፡ ያክብሩ ።

፯፻፳፱ ድስቅ ፡ ፴ ፡ በክቡር ፡ ደሙ ፡ የዋጃችሁ ፡ ወንድ ሞቼ ፡ ሆይ ፡ ይኸውም ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ደም ፡ ነው ፤ ቂጣን ፡ ከመብላት ፡ በኋላ ፡ በፍ ጹም ፡ ትጋትና ፡ በታላቅ ፡ አሳብ ፡ በዓለ ፡ ፋሲ ካን ፡ ታከብሩ ፡ ዘንድ ፡ ይገባችኋል ። ይህን ፡ የጌታን ፡ የመከራውን ፡ መታሰቢያ ፡ በዓል ፡ በአንድ ፡ ዓመት ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ አታድርጉ ፡ ስለእኛ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ስለሞተ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አድርጉ ፡ እንጂ ።

፯፻፴ ከአይሁድ ፡ በዓል ፡ በፍጹም ፡ ጥንቃቄ ፡ ተጠ በቁ ፡ ይኸውም ፡ በሚያዝያ ፡ ወር ፡ የሚሆን ፡

በዘመነ ፡ ሚያዝያ ፡ ወዘንተ ፡ ዕቀቡ ፡ እስከ ፡ ፳ወ፩ ፡ ዕለት ፡ እምወርኅ ፡ ከመ ፡ ኢይኩን ፡ አመ ፡ ፲ወ፬ ፡ ለሠርቀ ፡ ወርኅ ፡ በካልእ ፡ ሱባዔ ፡ ዘእንበለ፡ በሱባዔ ፡ ዘቦቱ ፡ ይገብሩ ፡ ፍሥሐ ።

፯፻፴፩ ወኢትግበሩ ፡ በዓለ ፡ ትንሣኤሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘእንበለ ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ ባሕቲቶ ፡ ወብልዑ ፡ ጊዜ ፡ ንቅወተ ፡ ዶርሆ ፡ ወእመ ፡ አኮ ፡ በነግህ ። ወኩኑ ፡ ትጉሃነ ፡ በይእቲ ፡ ሌሊት ፡ እንዘ ፡ አንትሙ ፡ ጉቡአን ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወእንዘ ፡ ትጼልዩ ፡ ወታነብቡ ፡ እምነ ፡ መዝሙራት ፡ ወትንቢታት ፡ ወአሪት ።

፯፻፴፪ ወእምድኅረ ፡ አጥመቅምዎሙ ፡ ለንኡሰ ፡ ክርስቲያን ፡ አንብቡ ፡ ወንጌላተ ፡ በፍርሃት ፡ ወበረዓድ ፡ ወንግርዎሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ዘይሜኒ ፡ ለመድኃኒቶሙ ፡ ወአዕርጉ ፡ ቍርባንክሙ ፡ ዘአዘዘክሙ ፡ በእንቲአሁ ፡ በላዕለ ፡ እደዊነ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ግበሩ ፡ ዘንተ ፡ ለተዝካርየ ።

፯፻፴፫ ወእምድኅረዝ ፡ ፍትሑ ፡ ጾመክሙ ፡ እንዘ ፡ ትትፌሥሑ ፡ ወትትኀሠዩ ፡ እስመ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ተንሥአ ፡ እምነ ፡ ሙታን፡ ወውእቱ ፡ ዓረቦነ ፡ ትንሣኤነ ። ወይኩን ፡ ለክሙ ፡ ሕገ ፡ ቀዋሜ ፡ ዝንቱ ፡ እስከ ፡ ኅልቀተ ፡ ዓለም ፡ ወእስከ ፡ ይመጽእ ፡ እግዚእነ ።

፯፻፴፬ ወእምድኅረ ፡ ሰሙን ፡ መዋዕል ፡ ግበሩ ፡ ለክሙ ፡ በዓለ ፡ እስመ ፡ በውእቱ ፡ ዕለት ፡ አመረኒ ፡ ሊተ ፡ ለቶማስ ፡ እግዚእነ ፡ ሶበ ፡ ኢአመንኩ ፡ በትንሣኤሁ   ወአርአየኒ ፡ አሠረ ፡ ቅንዋት ፡ ወአሠረ ፡ ርግዘት ፡ ዘገቦሁ ።

፯፻፴፭ ወእምነ ፡ ቀዳሚት ፡ ዕለት ፡ እምሰሙን ፡ ቀዳማዊ ፡ ኈልቁ ፡ ፵ ፡ ዕለተ ፡ እስከ ፡ ኃምስ ፡ ሰንበት ።

፯፻፴፮ ወእምዝ ፡ ግበሩ ፡ በዓለ ፡ ዕርገቱ ፡ ለእግዚእነ ፡ ወመድኃኒነ ፡ ዘቦቱ ፡ ፈጸመ ፡ ኵሎ ፡ ሥርዓታተ ፡ ወኵሎ ፡ መዓርጋተ ፡ ወዐርገ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ዘፈነዎ ፡ ወነበረ ፡ በየማነ ፡ ኀይል ።

፯፻፴፯ ወእምድኅረ ፡ ፲ቱ ፡ መዋዕል ፡ እምበዓለ ፡ ዕርገት ፡ ወውእቱ ፡ ዕለት ፡ እምእመ ፡ ተኈለቈ ፡ ሰሙነ ፡ ፋሲካ ፡ ይከውን ፡ ፶ ፡ መዋዕለ ፡ ወይኩን ፡ ለክሙ ፡ በዓለ ፡ ዐቢየ ፡ እስመ ፡ በውእቱ ፡ ዕለት ፡ ጊዜ ፡ ፫ቱ ፡ ሰዓት ፡ ፈነወ ፡ ለነ ፡



የቂጣ ፡ በዓል ፡ ነው ። ፍሥሕን ፡ (ተድላ ፡ ደስታን) ፡ በሚያደርጉበት ፡ ሳምንት ፡ በቀር ፡ በሁለተኛው ፡ ሳምንት ፡ ጨረቃ ፡ በወጣች ፡ በ፲፬ ፡ ቀን ፡ እንዳይሆን ፡ ከወሩ ፡ ጀምራችሁ ፡ እስከ ፡ ኻያ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ይህን ፡ ጠብቁ ።

፯፻፴፩ የጌታችን ፡ የመድኃኒታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ትንሣኤ ፡ ከዕለተ ፡ እሑድ ፡ ብቻ ፡ በስተቀር ፡ አታድርጉ ። ዶሮ ፡ በጮኸም ፡ ጊዜ ፡ ብሉ ፡ ይህም ፡ ባይሆን ፡ በጥዋት ፡ ብሉ ። እናንተ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተሰብስባችሁ ፡ በዚያች ፡ ሌሊት ፡ የተጋችሁ ፡ ሁኑ ፡ እየጸለያችሁ ፡ ከመዝሙሩ ፡ ከነቢያቱ ፡ ከኦሪቱም ፡ እያነበባችሁ ።

፯፻፴፪ ንኡሰ ፡ ክርስቲያንን ፡ ካጠመቃችኋቸው ፡ በኋላ በፍርሃትና ፡ በመንቀጥቀጥ ፡ ወንጌልን ፡ አንብቡ ። ለድኅነታቸውም ፡ የሚበጃቸውን ፡ ለሕዛብ ፡ ንገሯቸው ። ለመታሰቢያዬ ፡ ይህን ፡ አድርጉ ፡ ሲል ፡ በእኛ ፡ ቃል ፡ ስለርሱ ፡ ያዘዛችሁን ፡ መሥዋዕታችሁን ፡ ሠዉ ።

፯፻፴፫ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ እያላችሁ ፡ ጾማችሁን ፡ ፍቱ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ ተነሥቷልና ፤ ይኸውም ፡ የትንሣኤያችን ፡ ዓረቦን ፡ ነው ። ይህ ፡ ዓለም ፡ እስኪያልፍ ፤ ጌታችንም ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ የጸና ፡ ሕግ ፡ ይሁንላችሁ ።

፯፻፴፬ ከስምንት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ በዓል ፡ አድርጉ ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ ትንሣኤውን ፡ ባላመንኩ ፡ ጊዜ ፡ የችንካሮችን ፡ ምልክትና ፡ የጐኑን ፡ መወጋት ፡ ምልክት ፡ አሳይቶ ፡ ለእኔ ፡ ለቶማስ ፡ አስረድቶኛልና ።

፯፻፴፭ ከመጀመሪያው ፡ ሳምንት ፡ ከመጀመሪያይቱ ፡ ቀን ፡ ጀምራችሁ ፡ እስከ ፡ አምስት ፡ ሱባኤ ፡ ቀን ፡ ቁጠሩ ።

፯፻፴፮ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሥርዓቱንና ፡ መዓርጋቱን ፡ ሁሉ፡ የፈጸመበትንና ፤ ወደላከው ፡  ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ያረገበትን ፤ በአብ ፡ ቀኝ ፡ የተቀመጠበትን ፡ የጌታችንና ፡ የመድኃኒታችንን ፡ በዓለ ፡ ዕርገት ፡ አድርጉ ፡ (አክብሩ) ።

፯፻፴፯ ከበዓለ ፡ ዕርገት ፡ ቀጥሎ ፡ ከአሥር ፡ ቀን ፡ በኋላ ይኸውም ፡ ቀን ፡ ሰሙነ ፡ ፋሲካ ፡ ከተቆጠረበት ጀምሮ ፡ ፶ ፡ ቀን ፡ ይሆናል ፡ ታላቅ ፡ በዓል ፡ ይሁንላችሁ ። በዚያ ፡ ዕለት ፡ በ፫ ፡ ሰዓት ፡ ጌታችን፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አጽናኝ ፡ የሆነውን ፡ የዕው

እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጰራቅሊጦስሃ ፡ መንፈስ ፡ ጽድቅ ፡ ወተመላእነ ፡ እምፈቃዳ ቲሁ ፡ ወተናገርነ ፡ በልሳናት ፡ ሐዲሳት ፡ በከመ ተሐውሰ ፡ ውስቴትነ ፡ ወሰበክነ ፡ ለአይሁድ ፡ ወለአሕዛብ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚ እብሔር ፡ ውእቱ ።

ነት ፡ መንፈስ ፡ በዶልናልና ፡ ከፈቃዱም ፡ የተ ነሣ ፡ ተመላን ፡ በእእምሮእችን ፡ እንደአደረብን መጠን ፡ በአዲሶች ፡ ቋንቋዎች ፡ ተናገርን ፡ እርሱ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደሆነ ፡ ለአይሁድና ፡ ለአሕዛብም ፡ አስተማርን ።

፲፻፴፰ ወእምድኅረ ፡ ፈጸምክሙ ፡ ገቢረ ፡ በዓለ ፡ ፶ ፡ አብዕሉ ፡ ሰቡዐ ፡ መዋዕለ ፡ ካልአ ፡ እስመ ፡ ይደሉ ፡ ለነ ፡ ከመ ፡ ንትፈሣሕ ፡ በሀብተ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ እንተ ፡ ተውህበት ፡ ለነ ።

፲፻፴፰ በዓለ ሃምሳን ፡ አክብራችሁ ፡ ከጨረሳችሁ ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ በባት ፡ ቀን ፡ በዓል ፡ አድርጉ ። ለእኛ ፡ በተሰጠችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስጦታ ፡ ደስ ፡ ሊለን ፡ ይገባልና ።

፲፻፴፱ ወዘሰ ፡ ይጸውም ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ ዘውእቱ ፡ ዕለተ ፡ ትንሣኤ ፡ ኃጥእ ፡ ውእቱ ፡ ወይደልዎ ፡ ኵነኔ ። ወከማሁ ፡ ዘይገብር ፡ በመዋዕለ ፡ ፶ ፡ እው ፡ ዘየኀዝን ፡ በዕለተ ፡ በዓላት ፡ ዘእግዚእነ ፡ ዘይደሉ ፡ ለነ ፡ ፍሥሓ ፡ መንፈሳዊ ፡ በሙ ፡ ወአኮ ፡ ኀዘን ።

፲፻፴፱ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ የሚጸም ፡ ግን ፡ ኃጢአተኛ ፡ ነው ፡ ይኸውም ፡ የትንሣኤ ፡ ዕለት ፡ ነው ፡ ቅጣትም ፡ ይገባዋል ። በመዋዕለ ፡ ፶ ፡ የሚ ጾም ፡ ወይም ፡ ኀዘን ፡ ያይደለ ፡ መንፈሳዊ ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ልናደርግባቸው ፡ በሚገባን ፡ በጌታ ፡ በዓላት ፡ ቀን ፡ የሚያዝን ፡ እንደዚሁ ፡ ቅጣት ፡ ይገባዋል ።

፲፻፵ ረስጣ ፡ ፳ወ፯ቱ ፡ ወኢትግበሩ ፡ በበሙነ ፡ ሕማ ማት ፡ ወኢበዘይመጽእ ፡ እምድኅሬሁ ፡ ዘው እቱ ፡ በዓል ፡ ፩ዱ ፡ በእንተ ፡ ዘተሰቅለ ፡ ቦቱ ፡ እግዚእነ ፡ ወካልኡሂ ፡ በእንተ ፡ ዘተንሥአ ፡ ቦቱ ፡ እሙታን ። ወኢትግበሩ ፡ በዕለተ ፡ በዓለ ፡ ዕርገት ፡ እስመ ፡ ሥርዓተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተፈ ጸመ ፡ ቦቱ ። ወኢትግበሩ ፡ በዕለተ ፡ በዓለ ፡ ፶ ፡ እስመ ፡ ቦቱ ፡ ተከሥተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዝንቱ ፡ ዘወረደ ፡ ላዕለ ፡ ምእመናን ፡ በክርስ ቶስ ። ወኢትግበሩ ፡ በበዓለ ፡ ልደቱ ፡ ለክርስ ቶስ ፡ እስመ ፡ ጸጋ ፡ ተውህበት ፡ ቦቱ ፡ ለእጓለ ፡ እመሕያው ። ወኢትግበሩ ፡ በበዓለ ፡ ጥምቀት ፡ እስመ ፡ ቦቱ ፡ ከሠተ ፡ ክርስቶስ ፡ መለኮቶ ፡ ወስምዐ ፡ ኮነ ፡ ሎቱ ፡ አብ ፡ በጥምቀቱ ፡ ወወ ረደ ፡ ላዕሌሁ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በእምሳለ ፡ ርግብ ፡ ወከሠተ ፡ ለእለ ፡ ይቀውሙ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጽድቅ ፡ ወወልደ ፡ እግዚአብሔር ። ወኢትግበሩ ፡ በዕለተ ፡ በዓለ ፡ ሐዋርያት ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ኮኑ ፡ ለክሙ ፡ መምህራነ ፡ ለአእምሮተ ፡ ክርስቶስ ፡ ወረሰዩ ክሙ ፡ ድልዋነ ፡ ከመ ፡ ትሳተፉ ፡ ሀብተ ፡ መን ፈስ ፡ ቅዱስ ።

፲፻፵ ረስጣ ፡ ፳፯ ፡ በሰሙነ ፡ ሕማማት ፡ ከርሱም ፡ ቀጥሎ ፡ በሚመጣው ፡ በዓል ፡ ሥራ ፡ አትሥሩ። ይኸውም ፡ አንዱ ፡ በዓል ፡ ጌታችን ፡ ስለተሰቀ ለበት ፡ ሁለተኛውም ፡ ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ በለተነሣበት ፡ ነው ። በበዓለ ፡ ዕርገት ፡ ቀን ፡ ሥራ ፡ አትሥሩ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሥርዓት ፡ ተፈጽሞበታልና ፡ በበዓለ ፡ ፶ ኛው ፡ ቀን ፡ ሥራ አትሥሩ ። በክርስቶስ ፡ ባሙኑ ፡ ምእመናን ፡ ላይ ፡ የወረደ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተገልጦበታ ልና ። በክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በዓል ፡ አትሥሩ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ክብር ፡ ተሰጥታበታለችና ። በበዓለ ፡ ጥምቀት ፡ አትሥሩ ፡ ክርስቶስ ፡ መለ ኮቱን ፡ ገልጦበታልና ፡ በመጠመቁም ፡ አብ ፡ መሰከሮለታልና ፡ በርግብም ፡ አምሳል ፡ መን ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ወርዷልና ፡ ለቆሙት ሰዎች ፡ በእውነት ፡ እግዚአብሔርና ፡ የእግዚ አብሔር ፡ ልጅ ፡ እንደሆነ ፡ ገልጦላቸዋልና ። በሐዋርያት ፡ በዓል ፡ ቀን ፡ አትሥሩ ፡ ክርስቶ ስን ፡ ለማወቅ ፡ መምህሮች ፡ ሁነዋችኋልና ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስንም ፡ ለመቀበል ፡ ዝግጁዎች ፡ አድርገዋችኋልና ።

፲፻፵፩ ወናሁ ፡ ተነግረ ፡ በአንቀጸ ፡ ምጽዋት ፡ ከመ ፡ ኢትትረአዩ ፡ በዕለተ ፡ በዓላት ፡ ቅድመ ፡ እግዚ አብሔር ፡ እግዚእክሙ ፡ ዕሩቃኒክሙ ። ወይቱ ልዎ ፡ ለዝንቱ ፡ አንቀጽ ፡ ዘነበረ ፡ በእንተ ፡

፲፻፵፩ በበዓል ፡ ቀን ፡ በፈጣሪያችሁ ፡ በእግዚአብሔር ፊት ፡ ባዶ ፡ እጃችሁን ፡ ሁናችሁ ፡ እንዳትታዩ ፡ እነሆ ፡ በአንቀጸ ፡ ምጽዋት ፡ ተነገረ ። (ፍ ፡ ነገ ፡ ፲፯ ፡ ፲፻፴፩) ። የልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ የክበረ፡

ተሠውጦ ፡ ኀበ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ክቡር ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፨

፯፻፶፪ መከ ፡ ፻፳ወ፭ዱ ፡ ወዘተከህሎ ፡ እምኔክሙ ፡ ጸሊዮ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሀገረ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንተ ፡ ውስቴታ ፡ አሠረ ፡ ቅድሳት ፡ ኢይደኀር ፡ እምዝንቱ ፡ በምንትኒ ፡ ምክንያት ፡ ዘይክልእ ፡ ዘእንበለ ፡ በግብር ፡ ከመ ፡ የሐውጽ ፡ መካናተ ፡ ዘበሙ ፡ ተወክፈ ፡ እግዚእነ ፡ ክርስቶስ ፡ ሕማማተ ፡ በሥጋሁ ፡ ወይርአይ ፡ መካነ ፡ ትንሣኤሁ ፡ ወይትባረክ ፡ በእሙንቱ ፡ አሠራተ ፡ እምላካውያት ።

፯፻፶፫ ወዘሰ ፡ ኢተክህሎ ፡ ይፈኑ ፡ ኀቤሃ ፡ ቍርባናተ ፡ በአምጣነ ፡ ክሂሎቱ ፡ በእንተ ፡ ሥርዓታ ፡ ወበ ዘይትረድኡ ፡ ቦቱ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስቴታ ፡ እመኒ ፡ ወርቀ ፡ አው ፡ ብሩረ ፡ አው ፡ አልባሳተ ፡ አው ፡ መጻሕፍተ ፡ ውኩፋተ ፡ ወዘይመስሎ ፡ ለዝንቱ ። ወይኩን ፡ ላቲ ፡ ክፍል ፡ እምነ ፡ ርስቶሙ ፡ ለመሃይምናን ፡ እለ ፡ አዕረፉ ፡ ከመ ፡ ወራስያኒሆሙ ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ሕግ ፡ ሠናይ ፡ ውእቱ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይኩኑን ፡ ሎቱ ፡ ጸጋ ፡ በሀገረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅድስት ፡ ወቍርባነ ፡ ኅሩየ ፡ ወውኩፈ ፡ ዘይትዌከፎ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ።

ስለ ፡ ሰማዕታት ።

ቤት ፡ ወደሚሆን ፡ ወደኢየሩሳሌም ፡ ስለመሄድ ፡ የተጻፈው ፡ ይህን ፡ አንቀጽ ፡ ይመለከታል ።

፯፻፶፪ መከ ፡ ፻፳፩ ፡ ከእናንተ ፡ ወገን ፡ የቅድሰና ፡ ፍሊጋ ፡ በውስጧ ፡ በሚገኝባት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ለመጸለይ ፡ ፈቃድ ፡ ያለው ፡ ቢኖር ፡ በሚከለክል ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ከዚህ ፡ ወደኋላ ፡ አይበል ፡ በግድ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ። ጌታችን ፡ ክርስቶስ ፡ በሥጋው ፡ መከራ ፡ የተቀበለባቸውን ፡ ቦታዎች ፡ ይጐበኝ ፡ ዘንድ ፡ የትንሣኤውን ፡ ቦታ ፡ አይቶ ፡ በእነዚህ ፡ በአምላካውያት ፡ ምልክቶች ፡ ይባረክ ፡ ዘንድ ።

፯፻፶፫ መሄድ ፡ የማይቻለው ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ስለአስተዳደሯ ፡ በውስጧም ፡ የሚኖሩት ፡ ሰዎች ፡ በሚረዱበት ፡ ገንዘብ ፡ የተቻለውን ፡ ያህል ፡ መባ ፡ ይስደድ ፡ ወርቅ ፡ ብር ፡ ወይም ፡ ልብስ ፡ ወይም የተቀበሏቸውን ፡ መጻሕፍት ፡ ይሁን ፡ የሚመስለውንም ፡ ቢሆን ። ከሞቱት ፡ ከክርስቲያኖች ፡ ርስት ፡ እንደ ፡ ወራሾቻቸው ፡ መካፈል ፡ ይገባታል ። ይህ ፡ ሕግ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የተወደደ ፡ ነውና ፡ ቅድስት ፡ በምትሆን ፡ በእግዚአብሔር ፡ አገር ፡ ክብር ፡ የተመረጠ ፡ መሥዋዕት ፡ እግዚአብሔር ፡ አብና ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ የሚቀበለው ፡ ስጦታ ፡ ይሆንለታል ።

## አንቀጽ ፡ ፳ ።

በእንተ ፡ ሰማዕታት ፡ ወተአማንያን ፡ ወከሃድያን ።

፯፻፶፬ ድስቅ ፡ ፳ወ፪ቱ ፡ ሰማዕታት ፡ ይኩኑ ፡ ኀቤክሙ ፡ ክቡራነ ፡ በከመ ፡ ኮኑ ፡ ክቡራነ ፡ በኀቤነ ፡ ብፁዕ ፡ ያዕቆብ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወቅዱስ ፡ እስጢፋኖስ ፡ ሱታፌነ ፡ ዲያቆን ፡ እሉ ፡ እሙንቱ ፡ እለ ፡ ተበፅዑ ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወትሩፋቲሆሙ ፡ ዘኢይትረከብ ።

፯፻፶፭ ዘ፳ወ፫ቱ ፡ ለክርስቲያናዊ ፡ ዘይወድይዎ ፡ ዐላውያን ፡ ውስተ ፡ ሁከት ፡ በእንተ ፡ ስመ ፡ እግዚእነ ፡ ወሃይማኖት ፡ ርትዕት ፡ ወፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢትትዐበዩ ፡ በእንቲአሁ ፡ እላ ፡ እምጸማክሙ ፡ ዘበአማን ፡ ወእምሐፈ ፡ ገጽ ፡

## አንቀጽ ፡ ፳ ።

ስለ ፡ ሰማዕታት ፡ ስለ ፡ አማንያን ፡ ስለ ፡ ከሃድያን ።

፯፻፶፬ ድስቅ ፡ ፳፪ ፡ ብፁእ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ያዕቆብና ፡ ተባባሪያችን ፡ ዲያቆን ፡ ቅዱስ ፡ እስጢፋኖስ ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ የከበሩ ፡ እንደሆኑ ፡ ሰማዕታት ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ የከበሩ ፡ ይሁኑ ። እነዚህም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የተመሰገኑ ፡ ናቸው ። ትሩፋታቸውም ፡ የማይገኝ ፡ ነው ።

፯፻፶፭ ፳፫ ፡ ስለጌታችን ፡ ስምና ፡ ስለ ፡ ቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ ስለእግዚአብሔርም ፡ ፍቅር ፡ ዐላውያን ፡ በቅጣት ፡ የሚያሰቃዩትን ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ስለርሱ ፡ ትል ፡ አትበሉ ። በእውነት ፡ ወዛችሁ ፡ ተንጠፍጥፎ ፡ ካገኛችሁት ፡ ገንዘባችሁ ፡ ኀይ

ከሙ ፡ ፈንወ ፡ ኀቤሁ ፡ ዘይፈቅድ ፡ ከመ ፡ ይር ከብ ፡ ኀይለ ፡ ወዘይሁቦሙ ፡ ለሐራ ፡ እለ ፡ የዐ ቅብዎ ፡ በእንተ ፡ ዓስቦሙ ፡ ከመ ፡ ይርከብ ፡ ዕረፍተ ፡ በኀቤሆሙ ። ወውእቱ ፡ ስማዕት ፡ ቅዱስ ፡ ወእኁሁ ፡ ለክርስቶስ ፡ ወወልደ ፡ ልዑል ፡ ወማኅደረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወሰማ ዕተ ፡ ሕማሙ ፡ ለክርስቶስ ፡ ወሱታፌ ፡ ለእ ርእየ ፡ ስብሐቲሁ ።

፯፻፺፮ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ እንትሙኒ ፡ አ ፡ ማኅበረ ፡ መሃ ይምናን ፡ ተለእክዎሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ በመዛግብ ቲክሙ ፡ ወበጻማክሙ ። ወለእመኒ ፡ ኮነ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔክሙ ፡ ዘእልቦቱ ፡ ምንትኒ ፡ ይጹም ፡ በእ ንቲአሆሙ ፡ ወይረሲ ፡ መንፈቀ ፡ ሲሳዩ ፡ ኵሎ፡ ዕለተ ፡ ለቅዱሳን ። ወዘሰ ፡ ሀሎ ፡ ውስተ ፡ ስፍሐ ፡ ብዕል ፡ ወብዝኀ ፡ ጥሪት ፡ ያጽግቦሙ ፡ እምስፍሐ ፡ ብዕሉ ፡ ወጥሪቱ ፡ ወነሶሉ ፡ ዘያ ሁብ ፡ እምዘ ፡ አጥረየ ፡ ለመድኀኒቶሙ ፡ እማ እስራቲሆሙ ፡ ይከውን ፡ ብፁዐ ፡ ወዓርከ ፡ ክር ስቶስ ፡ ይሰመይ ።

፯፻፺፯ ወሰማዕታትሰ ፡ እሉ ፡ እሙንቱ ፡ ዘይቤ ፡ ክርስ ቶስ ፡ በእንቲአሆሙ ፡ ዘሰ ፡ አምነኒ ፡ በቅድመ ፡ ሰብእ ፡ አአምኖ ፡ አነኒ ፡ በቅድመ ፡ አቡየ ፡ ዘበ ሰማያት ። ወለእመ ፡ ተሳተፍክምዎሙ ፡ በጊዜ ፡ ኀዘናቲሆሙ ፡ ይከውን ፡ ለክሙ ፡ ሰምዐ በእ ንተ ፡ ጸሕቀ ፡ ሕሊናክሙ ።

፯፻፺፰ ወለእመ ፡ ረከቦ ፡ ለ፩ዱ ፡ እምእለ ፡ ይትራድኦ ምሙ ፡ ለሰማዕት ፡ ኵነኔ ፡ ብፁዕ ውእቱ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ኮነ ፡ ሱታፌሆሙ ፡ ለሰማዕ ታት ፡ ወተመሰሎ ፡ ለክርስቶስ በሕማማቲ ሁ ፡ ሰነኒ ፡ ካዕበ ፡ ረከበነ ፡ ዝብጠት ፡ ብዙኀ ፡ እምካህናት ፡ ወኮነ ፡ ንወፅእ ፡ እምኀቤሆሙ ፡ እንዘ ፡ ንትፌሣሕ ፡ እስመ ፡ ደለወነ ፡ ከመ ፡ ንሕ ምም ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ፡ መድኀኒነ ። ወተፈ ሥሑኬ ፡ አንትሙሂ ፡ ሶበ ፡ ሐመምክሙ ፡ ከመዝ ፡ እስመ ፡ አንትሙ ፡ ትከውኑ ፡ ብፁዓነ ፡ በዕለተ ፡ ደይን ።

፯፻፺፱ ወለእለሂ ፡ ይሰድድዎሙ ፡ በእንተ ፡ ሃይማኖት ፡ ወይጕይዩ ፡ እምሀገር ፡ ውስተ ፡ ሀገር ፡ በእንተ፡ ትእዛዘ ፡ እግዚእነ ፡ ተወከፍዎሙ ፡ ወአዕርፍ ዎሙ ። ወርብኅዎሙ ፡ ወአክብርዎሙ ፡ ከመ ፡ ሰማዕታት ። ወተፈሥሑ ፡ ሶበ ፡ ተወከፍክም ዎሙ ፡ እንትሙ ፡ እስመ ፡ እግዚእ ፡ ክርስቶስ ፡



ልን ፡ ያገኝበት ፡ ዘንድ ፡ የሚሻውን ፡ በእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ዕረፍትን ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡ ስለዋጋቸው ፡ ለሚጠብቁት ፡ ጭፍራዎች ፡ የሚሰጣቸውን ፡ ላኩለት ፡ እንጂ ፡ ይኸውም ፡ ቅዱስ ፡ ሰማዕት ፡ የክርስቶስ ፡ ወንድም ፡ የልዑል ፡ ልጅ ፡ የመን ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ማደሪያ ፡ የክርስቶስ ፡ የመከራው፡ ምስክር ፡ የጌትነቱ ፡ እርእዩ ፡ ተባባሪ ፡ ነው ።

፯፻፺፮ ስለዚህ ፡ እናንተ ፡ የምእመናን ፡ ወገኖች ፡ ሆይ ፡ በገንዘባችሁና ፡ በድካማችሁ ፡ ቅዱሳንን ፡ እገ ልግሏቸው ። ከእናንተ ፡ ወገን ፡ አንዱ ፡ ምንም ፡ የሌለው ፡ ቢሆን ፡ ስለእነርሱ ፡ ይጹም ። ዘወ ትር ፡ የምግቡን ፡ እኩሌታ ፡ ለቅዱሳን ፡ ያድ ርግ ፡ (ይስጥ) ። ብዙ ፡ ብዕልና ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ከብዙ ፡ ብዕሉና ፡ ገንዘቡ ፡ የተነሣ ፡ ያጥግባቸው ። እነርሱን ፡ ከእስራታ ቸው ፡ ለመፍታት ፡ ከገንዘቡ ፡ ሁሉ ፡ የሚሰጥ ፡ ሰው ፡ ብፁዕ ፡ ይሆናል ፡ የክርስቶስም ፡ ፍጹም ፡ ባለሟል ፡ ይባላል ።

፯፻፺፯ ሰማዕታትም ፡ እኔን ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ ያመነኝን ፡ ሰው ፡ ግን ፡ እኔም ፡ በሰማይ ፡ አባቴ ፡ ፊት ፡ እምነዋለሁ ፡ ብሎ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለእነርሱ ፡ የተ ናገረላቸው ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። (ማቴ ፡ ፲ ፡ ፴፪) ። በመከራቸው ፡ ጊዜ ፡ ብትመስሏቸው ፡ ስለቁ ርጥ ፡ አሳባችሁ ፡ ሰማዕትነት ፡ ይቆጠርላች ኋል ።

፯፻፺፰ ሰማዕታትን ፡ ከሚረዱዋቸው ፡ ወገን ፡ አንዱ ፡ መከራ ፡ ቢያገኘው ፡ ብፁዕ ፡ ነው ፡ እርሱ ፡ የሰ ማዕታት ፡ ተባባሪያቸው ፡ ነውና ፡ በመከራዎ ቹም ፡ ክርስቶስን ፡ መስለው ። እኛንም ፡ ከካህ ናት ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ እገኘን ፡ ከእነርሱም ፡ ዘንድ ፡ ደስ ፡ እያለን ፡ ወጣን ፡ ስለመድኀኒ ታችን ፡ ስለክርስቶስ ፡ መከራን ፡ እንቀበል ፡ ዘንድ ፡ እደሎናልና ። (የሐዋ ፡ ፭ ፡ ፵፩) ። እናን ተም ፡ እንደዚህ ፡ መከራ ፡ በተቀበላችሁ ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ፡ እናንተ ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ትመ ሰገናላችሁና ።

፯፻፺፱ ስለሃይማኖት ፡ የሚያሳድዷቸውን ፡ ስለጌታ ችን ፡ ትእዛዝ ፡ ከእገር ፡ ወደእገር ፡ የሚሸሹትን ተቀበሏቸው ፡ እሳርፉዋቸውም ፡ ጥተሟቸ ውም ፡ እንደ ፡ ሰማዕታትም ፡ እድርጋችሁ ፡ አክብሯቸው ። በተቀበላችኋቸውም ፡ ጊዜ ፡ እናንተ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ። ጌታ ፡ ክርስቶስ ፡

እንቀጽ ፡ ኛ ።

ይቤ ፡ ብፁዓን ፡ አንትሙ ፡ ሶበ ፡ ይሰድዱክሙ ፡ በእንቲአየ ፡ ተፈሥሑ ፡ ወተኃሠዩ ፡ እስመ ፡ ዕሤትክሙ ፡ ዐቢይ ፡ በሰማያት ፡ ወከማሁ ፡ ሰደድዎሙ ፡ ለነቢያት ፡ እምቅድሜክሙ ፡ ወእምከመሰ ፡ ኪያየ ፡ ሰደዱ ፡ ኪያክሙኒ ፡ ይሰድዱክሙ ፡ ካዕበ ፡ ወሶበ ፡ ይሰድፉክሙ ፡ እም ዛቲ ፡ ሀገር ፡ ጕዩ ፡ ውስተ ፡ ካልእታ ።

፩፻፺ ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ ይረክበክሙ ፡ በዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ምንዳቤ ፡ ወኀዘን ፡ ወያበውኡክሙ ፡ ኀበ ፡ ጉባኤ ፡ ወያበጽሑክሙ ፡ ኀበ ፡ ነገሥት ፡ ወመኳንንት ፡ በእንቲአየ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ስምዐ ፡ ለክሙ ፡ ወዘተዓገሠ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ውእቱ ፡ ይድኅን ፡ ወዘሰ ፡ ይክሕድ ፡ ነፍሶ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ኢኮነ ፡ ለክርስቶስ ፡ ወአፍቀራ ፡ ለነፍሱ ፡ ፈድፋደ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ ኢይረክብ ፡ ምሕረተ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ አብደረ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ዓርከሙ ፡ ለሰብእ ፡ ወጸላኢሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወህየንተ ፡ መንግሥት ፡ ቡርክት ፡ አፍቀረ ፡ ሎቱ ፡ እሳተ ፡ ዘለዓለም ። ወበእንቲአሁ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ ዘክሐደኒ ፡ በቅድመ ፡ ሰብእ ፡ ወወለጠ ፡ ስምየ ፡ አነሂ ፡ እክሕዶ ፡ ወእዌልጦ ፡ በቅድመ ፡ አቡየ ፡ ሰማያዊ ።

፩፻፺፩ ወከመዝ ፡ ይቤለነ ፡ ለአርዳኢሁ ፡ ዘያበድር ፡ አባሁ ፡ ወእሞ ፡ እው ፡ ወልዶ ፡ ዐወለቶ ፡ ፈድፋደ ፡ እምኔየ ፡ ኢይደሉ ፡ ሊተ ፡ ወዘኢያረ ፡ መስቀለ ፡ ሞቱ ፡ ወኢተለወኒ ፡ ኢይደሉ ፡ ሊተ ። ዘያፈቅራ ፡ ለነፍሱ ፡ ለይግድፋ ፡ ወዘሰ ፡ ገደፋ ፡ ለነፍሱ ፡ በእንቲአየ ፡ ይረክባ ። ምንተ ፡ ይበቍዖ ፡ ለሰብእ ፡ ለእመ ፡ ኵሎ ፡ ዓለመ ፡ ረብሐ ፡ ወነፍሶ ፡ ሐጕለ ፡ ወምንተ ፡ እምወሀበ ፡ ሰብእ ፡ ቤዛሃ ፡ ለነፍሱ ። ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ ኢትፍርህዎሙ ፡ ለእለ ፡ ይቀትሉ ፡ ሥጋክሙ ፡ ወለነፍስክሙሰ ፡ ኢይክሉ ፡ ቀቲሎታ ፡ አላ ፡ ፍርህዎ ፡ ለዘይክል ፡ ሠዐለ ፡ አኅጕሎ ፡ ነፍስ ፡ ወሥጋ ፡ ኅቡረ ፡ ውስተ ፡ እሳተ ፡ ገሃነም ።

፩፻፺፪ መፍትው ፡ ሳዕሌነ ፡ ንጸሊ ፡ ወትረ ፡ ከመ ፡ ኢንባእ ፡ ውስተ ፡ መንሱት ፡ ወእመኒ ፡ ተኀረይነ ፡ ለከዊነ ፡ ስምዐ ፡ ንጽናዕ ፡ ለተወክሎ ፡ ወንሕ

ስለ ሰማዕታት ።

"ስለእኔ ፡ ባሳደዷችሁ ፡ ጊዜ ፡ እናንተ ፡ ብፁዓን ናችሁ ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ፡ ዋጋችሁ ፡ በሰማይ ፡ ታላቅ ፡ ነውና ። እንደዚሁም ፡ ከእናንተ ፡ አስቀድመው ፡ የነበሩ ፡ ነቢያትን ፡ አሳደዷቸው ፡ እኔን ፡ ካሳደዱ ፡ ግን ፡ ዳግመኛም ፡ እናንተን ፡ ያሳድዷችኋል ፡ ከዚች ፡ አገር ፡ ቢያሳድዷችሁ ፡ ወደሌላይቱ ፡ አገር ፡ ሂዱ ፡ ብሏልና። (ማቴ ፡ ፭ ፡ ፲፩-፲፪ ። ማቴ ፡ ፲ ፡ ፳፫) ።

፩፻፺ ዳግመኛም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ መከራና ፡ ኀዘን ፡ ያገኛችኋል ፡ ወደ ፡ አደባባይ፡ ያገቧችኋል ፡ ለናንተ ፡ ምስክር ፡ ሊሆንላችሁ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ወደነገሥታቱና ፡ ወደመኳንንቱ ፡ ያደርሷችኋል ። እስከ ፡ መጨረሻው ፡ የታገሠ ፡ እርሱ ፡ ይድናል ። ለክርስቶስ ፡ እንዳልሆነ ፡ የሚክድ ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ ይልቅ ፡ ፈጽሞ ፡ ራሱን ፡ የወደደ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ይቅርታን ፡ አያገኝም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጠላት ፡ የሰዎች ፡ ወዳጅ ፡ ሊሆን ፡ ወድዷልና ። ስለተባረከችውም ፡ መንግሥት ፡ ፈንታ ፡ የዘለዓለም ፡ እሳትን ፡ ወድዷልና ። (ማቴ ፡ ፲ ፡ ፲፯ - ፳፫) ። ስለርሱም ፡ ጌታችን ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ የካደኝን ፡ ስሜንም ፡ የለወጠውን ፡ እኔም ፡ በሰማያዊ ፡ አባቴ ፡ ፊት ፡ እክደዋለሁ ፡ እለውጠዋለሁም ፡ አለ ። (ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፰ - ፱) ።

፩፻፺፩ እንደዚህም ፡ ለእኛ ፡ ለደቀመዛሙርቱ ፡ ከእኔ ፡ ይልቅ ፡ አባቱንና ፡ እናቱን ፡ ወይም ፡ ወንድ ፡ ልጁንና ፡ ሴት ፡ ልጁን ፡ የሚወድ ፡ እኔን ፡ አይመስለኝም ። የሞቱንም ፡ መከራ ፡ ተሸክሞ ፡ ያልተከተለኝ ፡ እኔን ፡ አይመስለኝም ፡ አለ ። ሰውነቱን ፡ የሚወድ ፡ ይጣላት ፡ ሰውነቱን ፡ የጣላት ፡ ግን ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ያገኛታል ። ሰው ፡ ዓለሙን ፡ ሁሉ ፡ ቢገዛ ፡ ነፍሱን ፡ ካጣ ፡ ምን ፡ ይጠቀመዋል ? ሰው ፡ ለነፍሱ ፡ ቤዛ ፡ ምን ፡ በሰጠ ፡ ነበር ። (ማቴ ፡ ፲ ፡ ፴፯ -፴፱ ማቴ ፡ ፲፮ ፡ ፳፮ - ፳፯) ። ዳግመኛም ፡ ሥጋችሁን ፡ የሚገሉትን ፡ ሰዎች ፡ አትፍሯቸው ፡ ነፍሳችሁን ፡ ግን ፡ መግደል ፡ አይቻላቸውም ፡ ነፍስና ፡ ሥጋን ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ በገሃነም ፡ እሳት ፡ መቅጣት ፡ የሚቻለውን ፡ ፍሩት ፡ እንጂ አለ ። (ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፬ -፭ ማቴ ፡ ፲ ፡ ፳፰) ።

፩፻፺፪ ወደፈተና ፡ እንዳንገባ ፡ ዘወትር ፡ መጸለይ ፡ ይገባናል ። (ማቴ ፡ ፳፮ ፡ ፵፩) ። ሰማዕት ፡ ለመሆንም ብንመረጥ ፡ በሃይማኖት ፡ እንጽና ፡ እኛም ፡ በከ

ነኒ ፡ እንዘ ፡ ንትእመን ፡ በስም ፡ ክቡር ፡ ዘው
እቱ ፡ ስሙ ፡ ለመድኃኒነ ። ወኢናንክር ፡ ሶበ ፡
ያስድዱነ ፡ ወኢናፍቅር ፡ ዘንተ ፡ ዓለመ ፡ ወክ
ብራቲሁ ፡ ወትምክሕተ ፡ ሰብእ ፡ ወኢንትወ
ከፍ ፡ ስብሐተ ፡ ብጡለ ፡ እምሊቃናት ፡ በእም
ላለ ፡ አይሁድ ፡ ዘኢክህሉ ፡ ከመ ፡ ይእመኑ ፡
እስመ ፡ አፍቀሩ ፡ ስብሐተ ፡ ሰብእ ፡ ፈድፋደ ፡
እምስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ።

በረ ፡ ስሙ ፡ እምነን ፡ ይኸውም ፡ የመድኃኒታ
ችን ፡ ስም ፡ ነው ፡ ባባረሩን ፡ ጊዜ ፡ እናድንቅ ፡
(እንጨነቅ) ። ይህን ፡ ዓለም ፡ ክብሩንም ፡
በሰው ፡ መመካትንም ፡ እንውደድ ። ያምኑ ፡
ዘንድ ፡ ባልቻሉ ፡ በአይሁድ ፡ እምሳል ፡ ከአለ
ቆች ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱን ፡ እንቀበል ። ከእግዚአ
ብሔር ፡ ምስጋና ፡ ይልቅ ፡ የሰው ፡ ምስጋናን ፡
ወድደዋልና ። (ዮሐ ፡ ፲፪ ፡ ፵፪ - ፵፫) ።

፩፻፺፫ ንትእመን ፡ ከመ ፡ ንድኀን ፡ ለሊነ ፡ ወናጽን
ዖሙ ፡ ለካልእኒነ ፡ ከመ ፡ ኢንኩን ፡ ምክንያተ ፡
ሐጕል ፡ ለባዕዳን ፡ ወኢንብጻሕ ፡ ኀበ ፡ ዡነኔ ፡
ሀየንተ ፡ ዝንቱ ፡ ወኢንመጡ ፡ ነፍሳቲነ ፡ ለመ
ከራ ፡ እስመ ፡ እግዚእነ ፡ ይቤ ፡ መንፈስስ ፡
ጥቡዕ ፡ ወሥጋ ፡ ድኩም ።

፩፻፺፫ እኛ ፡ እንድን ፡ ዘንድ ፡ እንመን ፡ ለሌሎቹ ፡ የጥ
ፋት ፡ ምክንያት ፡ እንዳንሆን ፡ ባልንጀሮቻች
ንን ፡ እናጽናቸው ። ስለዚህ ፡ ወደፍርድ ፡ እንዳ
ንገባ ፡ ሰውነታችንንም ፡ ለመከራ ፡ እንዳንሰጥ፡
ጌታችን ፡ መንፈስ ፡ ብርቱ ፡ ነው ፡ ሥጋ ፡ ግን ፡
ደካማ ፡ ነው ፡ ብሏልና ። (ማቴ ፡ ፳፮ ፡ ፵፩) ።

፩፻፺፬ ወእመ ፡ ተጽዕቅነ ፡ ኢንወልጥ ፡ ሃይማኖተነ ፡
በእንተ ፡ ፍርሃተ ፡ ዘመን ፡ ሕጹር ። ወለእመ ፡
ክሕደ ፡ ዕዱሃ ፡ ተስፋሁ ፡ ዘውእቱ ፡ ኢየሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወያፈርህ ፡
እምዝንቱ ፡ ሞት ፡ ዘይከውን ፡ ለዘመን ፡ ኅዳጥ ፡
እስመ ፡ ውእቱ ፡ ጌሠመ ፡ ለእመ ፡ ወድቀ ፡
ውስተ ፡ ደዌ ፡ ጽንዕት ፡ እንተ ፡ አልባቲ ፡
ፈውስ ፡ ይከውን ፡ ውፁእ ፡ እምዛቲ ፡ ሕይወት ፡
ወየኀጥእ ፡ ዘዝየ ፡ ወይነብር ፡ ለዓለም ፡ ውስተ ፡
ጽልመት ፡ እፍእዊ ፡ ኀበ ፡ ሀሎ ፡ ብካይ ፡ ወሐ
ቅየ ፡ ስነን ።

፩፻፺፬ ብንጨነቅም ፡ ኀላፊውን ፡ ዘመን ፡ ስለመፍራት
ሃይማኖታችንን ፡ እንለውጥ ። እንዱስ ፡ እንኳ ፡
አለኝታውን ፡ ቢክድ ፡ ይኸውም ፡ የእግዚአብ
ሔር ፡ ልጅ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ። ለጥቂ
ትም ፡ ዘመን ፡ ከሚሆነው ፡ ሞት ፡ የተነሣ ፡
ቢፈራ ፡ ድኅነት ፡ በሌለበት ፡ በጸናች ፡ ደዌ ፡
ነገ ፡ ቢያዝ ፡ ከዚች ፡ ሕይወት ፡ የተለየ ፡ ይሆ
ናል ። የወዲያውንም ፡ ዓለም ፡ ያጣል ፡ ልቅሶ ፡
ጥርስ ፡ ማፋጨት ፡ ባለበት ፡ በጨለማ ፡ ውስጥ ፡
ለዘለዓለሙ ፡ ይኖራል ።(ማቴ ፡ ፰ ፡ ፲፫) ።

፩፻፺፭ ወዘኒ ፡ ኢተጠምቀ ፡ ኢይኩን ፡ ሕሙመ ፡
ልብ ፡ እስመ ፡ ሕማሙ ፡ ዘፆሮ ፡ በእንተ ፡ ክርስ
ቶስ ፡ ውእቱ ፡ ይከውኖ ፡ ጥምቀተ ፡ ኅሩየ ፡
እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይመውት ፡ ምስለ ፡ እግዚእነ ፡
በጊዜ ፡ ነሥአ ፡ ምሳሌ ፡ ሞቱ ።

፩፻፺፭ ያልተጠመቀ ፡ ሰውም ፡ ልቡ ፡ አይዘን ። ስለክ
ርስቶስ ፡ የተቀበለው ፡ መከራ ፡ የተመረጠ ፡
ጥምቀት ፡ ይሆንለታልና ፡ የሞቱን ፡ ምሳሌ ፡
በተቀበለ ፡ ጊዜ ፡ በጌታ ፡ አምሳል ፡ ሞቷልና ።

፩፻፺፮ ረስጣ ፡ ፴ወ፪ቱ ፡ ኢይኩን ፡ ዘ፪ኤ ፡ ልቡ ፡
እስመ ፡ ለእመ ፡ ቀተልዎ ፡ ወእመ ፡ ውእቱ ፡
ተቀትለ ፡ ይጸድቅ ፡ እስመ ፡ ተጠምቀ ፡ በደሙ ፡
ባሕቲቱ ።

፩፻፺፮ ረስጣ ፡ ፴፪ ፡ ሁለት ፡ ልብ ፡ አይሁን ፡ እነርሱ ፡
ቢገድሉት ፡ እርሱም ፡ ቢገደል ፡ ይጸድቃልና ፡
በደሙ ፡ ብቻ ፡ ተጠምቋልና ።

፩፻፺፯ ዘዕንቀራ ፡ ይቱ ፡ ወእመቦ ፡ ብእሲ ፡ ዘጕየ ፡ በእ
ንተ ፡ ሃይማኖቱ ፡ ወሕገጋቲሁ ፡ ፈረሆ ፡ እምበ
ላውያን ፡ ወለእመ ፡ ወፅአ ፡ እምሃይማኖቱ ፡ በእ
ገብሮ ፡ ወእምድኅረዝ ፡ ከሠተ ፡ ንስሓሁ ፡ በን
ጽሕ ፡ እምዘ ፡ ኮነ ፡ ቅድመ ፡ በኵሉ ፡ ልቡ ፡
ወሕሊናሁ ፡ በትሕትና ፡ ጽኑዕ ፡ ወበአርእዮ ፡
ሕግ ፡ ኢይትከላእ ፡ እምነ ፡ ቍርባን ፡ ወእምበ
ዊእ ፡ ቅዳሴያት ፡ እመ ፡ ኮነ ፡ ካህነ ፡ እስመ ፡
ኢገብረ ፡ ዘንተ ፡ በፈቃዱ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡

፩፻፺፯ ዕንቀራ ፡ ከመናፍቃን ፡ የተነሳ ፡ ፈርቶ ፡ ስለሃይ
ማኖቱና ፡ ስለሕጉ ፡ ብሎ ፡ የሸሸ ፡ ሰው ፡ ቢኖር፡
በግድ ፡ ከሃይማኖቱ ፡ ቢወጣ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡
ቀድሞ ፡ የነበረበትን ፡ በንጽሕና ፡ በልቡና ፡
በአሳቡ ፡ ሁሉ ፡ በፍጹም ፡ ትሕትና ፡ ሕግንም ፡
በማመልከት ፡ ንስሐውን ፡ ቢገልጥ ፡ ካህን ፡
ቢሆን ፡ ከሥጋውና ፡ ከደሙ ፡ ቅዳሴ ፡ ከመግባ
ትም ፡ አይከልከል ። ይህን ፡ ወድዶ ፡ አላደረገ
ውምና ። መሐይምን ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ቤተ ፡ ክር

ምእመን ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይባእ ፡ ለመልእክተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወይኩን ፡ ካህን ። ወለእመ ፡ አልቦ ፡ ላዕሌሁ ፡ ዕቅፋት ፡ ዘአንበለ ፡ ዝንቱ ፡ ወእመ ፡ እዝለፈ ፡ ምግባረ ፡ ኂሩት ፡ ይኩን ፡ ምእመን ፡ በጸሎት ።

፳፻፶፰ ዘ፳ቱ ፡ ወዘሂ ፡ ክሕደ ፡ ፈሪሆ ፡ ቅድመ ፡ ይዝብጥዎ ፡ ወይንሥኡ ፡ ንዋዮ ፡ ወኢጸንዐ ፡ በሃይማኖቱ ፡ አመ ፡ ግብአቱ ፡ ኀቤነ ፡ የሀሉ ፡ ውስተ ፡ ንስሐ ፡ ብዙኀ ፡ መዋዕለ ፡ ወለእመ ፡ ተመይጠ ፡ በኵሉ ፡ ልቡ ፡ ወኀሠሠ ፡ ቍርባነ ፡ ያቅርብዎ ። ወለእመ ፡ ሐመ ፡ ሕማመ ፡ ወአልጸቀ ፡ ለመዊት ፡ ይትወከፍዎ ፡ በቍርባን ፡ ከመ ፡ ይትመየጥ ፡ ኀበ ፡ ንስሐሁ ፡ ሶበ ፡ ሐይወ ።

፳፻፶፱ ዘ፳፬ቱ ፡ ወለዘከመ ፡ አሉ ፡ ይትወከፍዎሙ ፡ እምድኅረ ፡ ነስሑ ፡ በዕድሜ ፡ ነዊኅ ፡ ወይኅበሩ ፡ ምስለ ፡ ምእመናን ፡ በዕሪና ፡ እስመ ፡ ሕግነ ፡ ሕገ ፡ ሣህል ፡ ወምሕረት ።

፳፻፷ ዘ፳ ፡ ወለዘኢአክሎ ፡ ክሕደቱ ፡ ባሕቲቱ ፡ እስከ ፡ ያወዕአ ፡ ለካልኡ ፡ እምሃይማኖቱ ፡ ወኮነ ፡ ምክንያተ ፡ ለክሕደቱ ፡ ይኩን ፡ ንስሐሁ ፡ ፈድፋደ ።

፳፻፷፩ ረስጠጅ ፡ ዘ፳ወ፩ዱ ፡ ወለኵሎሙ ፡ ዘከዐዉ ፡ ደሞሙ ፡ በእንተ ፡ ሃይማኖተ ፡ አግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ይግበሩ ፡ ሎሙ ፡ ተዝካረ ፡ በዕለት ፡ ዘስምዐ ፡ ኮኑ ፡ ባቲ ።

፳፻፷፪ በሲ ፡ ፴ወ፫ቱ ፡ ወመካነ ፡ ሰማዕታት ፡ ይኩን ፡ ታሕተ ፡ ሥልጣነ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሐቲ ፡ ጉባኤ ፡ አኮ ፡ ያአቲ ፡ ዘትሴባሕ ፡ በዓፅመ ፡ ሰማዕታት ፡ አላ ፡ ሰማዕታት ፡ ይነሥኡ ፡ ስብሐተ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እስመ ፡ ስብሐት ፡ ላቲ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በእንተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሐቲ ፡ ጉባኤ ፡ እንተ ፡ ተሐንጸት ፡ አመንገለ ፡ አበዊነ ፡ ሐዋርያት ፡ ቅዱሳን ።

፳፻፷፫ ዘ፶ቅያ ፡ ወያንብሩ ፡ አዕፅምቲሆሙ ፡ ለሰማዕታት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወምኔታት ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ እመካነ ፡ ሥጋቲሆሙ ፡ ፈውስ ፡ ወበቍዔት ፡ ለድዉያን ፡ ወለሕሙማን ፡ ወለሰብእ ፡ ፈቃድያነ ፡ በቍዔት ፡ ወመድኃኒት ።

፳፻፷፬ ወእለሰ ፡ ይፀርፉ ፡ ላዕለ ፡ አዕፅምቲሆሙ ፡ ለእሉ ፡ ንጹሓን ፡ ወያስተራክብዋ ፡ ናሁ ፡ ይጌሥፆሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ በተአምራት ፡ እንተ ፡ ትትገበር ፡ እምኔሆሙ ፡ ወመድኃኒት ፡ ለድዉያን ፡ ወፈ



ስቲያንን ፡ ለማገልገል ፡ ይገባ ፡ ዘንድ ፡ ይገባዋል ፡ ካህንም ፡ ይሁን ። ከዚህ ፡ በቀር ፡ ኃጢአት ፡ ባይኖርበት ፡ የቸርነትን ፡ ሥራ ፡ ቢያዘወትር ፡ በጸሎት ፡ የታመነ ፡ ይሁን ።

፳፻፶፰ ፳ ፡ ሳይመቱት ፡ ገንዘቡን ፡ ሳይወስዱበት ፡ አስቀድሞ ፡ ፈርቶ ፡ የካደ ፡ በሃይማኖቱ ፡ ያልጸና ፡ ሰው ፡ ወደእኛ ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ በንስሓ ፡ ይኑር ፡ በፍጹም ፡ ልቡ ፡ ቢመለስ ፡ ሊቆርብም ፡ ቢፈልግ ፡ ያቁርቡት ። ሕማም ፡ ቢታመም ፡ ግን ፡ ለሞትም ፡ ቢደርስ ፡ በዳነ ፡ ጊዜ ፡ ወደንስሓው ፡ ይመለስ ፡ ዘንድ ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ያቀብሉት ።

፳፻፶፱ ፳፬ ፡ እንዲህ ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ንስሐ ፡ ከገቡ ፡ በኋላ ፡ ይቀበሏቸው ፡ በክብር ፡ ከምእመናን ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ይሁኑ ፡ ሕጋችን ፡ የርኅራኄና ፡ የይቅርታ ፡ ሕግ ፡ ነውና ።

፳፻፷ ፳ ፡ የራሱ ፡ ክህደት ፡ ብቻ ፡ አልበቃው ፡ ብሎ ፡ ባልንጀራውን ፡ ከሃይማኖቱ ፡ እስኪያወጣው ፡ ድረስ ፡ ለመካድ ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፡ ንስሓው ፡ ጽኑዕ ፡ ይሁን ።

፳፻፷፩ ረስጠጅ ፡ ፳፩ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አምነው ፡ ደማቸውን ፡ ላፈሰሱ ፡ ሁሉ ፡ ባረፉበት ፡ ቀን ፡ መታሰቢያቸውን ፡ ያድርጉላቸው ።

፳፻፷፪ በስ ፡ ፴፫፡ የሰማዕታት ፡ መቃብር ፡ አንዲት ፡ በሆነች ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዙሪያ ፡ ይሁን ። እርሷ ፡ በሰማዕታት ፡ አጽም ፡ የምትከብር ፡ አይደለም ። ሰማዕታት ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ክብርን ፡ ይቀበላሉ ፡ እንጂ ። በአባቶቻችን ፡ በቅዱሳን ፡ ሐዋርያት ፡ እጅ ፡ ስለታነፀች ፡ አንዲት ፡ መሰብሰቢያ ፡ ስለምትሆን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንደተናገረ ፡ ክብር ፡ አላትና ።

፳፻፷፫ ኒቅያ ፡ የሰማዕታትን ፡ ዓጽም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ በገዳም ፡ ያኑሩ ፡ ሥጋቸው ፡ ከተቀበረበት ፡ ቦታ ፡ ለድዉያንና ፡ ለታመሙ ፡ ጥቅምንና ፡ ድኅነትን ፡ ለሚሹ ፡ ሰዎች ፡ ድኅነትና ፡ ጥቅም ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ።

፳፻፷፬ ንጹሓን ፡ የሚሆኑ ፡ የእነዚህን ፡ ዓጽም ፡ የሚሳደቡትንና ፡ የሚያረክሷትን ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ከርሷ ፡ በሚደረገው ፡ ተእምራት ፡ ድዉያንን ፡ በማዳን ፡ በሥጋና ፡ በነፍስ ፡ የታመሙትን ፡

ውሳት ፡ ለሕሙማን ፡ ነፍስ ፡ ወሥጋ ፡ ወስደተ ፡ ሰይጣናት ፡ እምኔሆሙ ።

፯፻፳፮ ማንር ፡ ፳ ፡ ወዘይሚንኖሙ ፡ ለእለ ፡ ይትጋብኡ ፡ በበዓለ ፡ ሰማዕታት ፡ ምሉእ ፡ ትዕቢት ፡ ውእቱ ፡ ውጉዝ ፡ ለይኩን ።

፯፻፳፯ ድስቅ ፡ ፴ወ፳ቱ ፡ ኢይደልዎሙ ፡ ለምእመ ናን ፡ ከመ ፡ ይኅድጉ ፡ ሰማዕታተ ፡ ክርስቶስ ፡ ወይሑሩ ፡ ኀበ ፡ መካነ ፡ ሰማዕታት ፡ ዘዐላው ያን ፡ ወናሁ ፡ ጸሐፈ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ዘከመ ፡ እፎ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ተጋድሎ ትነ ፡ በእንተ ፡ ፍቅሩ ፡ ለክርስቶስ ፡ ወይቤ ፡ በመልእክቱ ፡ ኀበ ፡ ሰብእ ፡ ሮሜ ፡ ፰ቱ ፡ መኑ ፡ ያኀድገነ ፡ ፍቅሮ ፡ ለክርስቶስ ፡ ምንዳቤኑ ፡ ተሞቅሖኑ ፡ ተሰዶኑ ፡ ረኃብኑ ፡ ዕርቃንኑ ፡ ተጋ እዞኑ ፡ መጥባሕትኑ ፡ በከመ ፡ ጽሑፍ ፡ "እስመ በእንቲአከ ፡ ንሞት ፡ ኵሎ ፡ አሚረ ፡ ወኮነ ፡ ከመ ፡ እጓል ፡ ዘይጠብሑ" ። ወበዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ ምንዳቤ ፡ ንሕነ ፡ መዋዕያን ፡ በእፍቅ ሮቱ ፡ ለዘአፍቀረነ ፡ ወአንሰ ፡ እትአመን ፡ ከመ እልቦ ፡ ዘይክል ፡ ይፍልጠኒ ፡ ኢ ፡ ሞት ፡ ወኢ ፡ ሕይወት ፡ ኢ ፡ መላእክት ፡ ወኢ ፡ ሊቃ ናት ፡ ወኢኵሉ ፡ ግብር ፡ ዘሀለወ ፡ ወዘሀለዎ ፡ ይምጻእ ፡ ወኢ ፡ ኀይላት ፡ ወኢ ፡ መልዕልት ፡ ወኢ ፡ ማዕምቅት ፡ ወኢ ፡ ካልእ ፡ ፍጥረት ፡ ዘበታሕቱ ፡ ኢይክል ፡ ይፍልጠኒ ፡ እምፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስ ቶስ ።

፯፻፳፰ ወናሁ ፡ ፈጸመ ፡ ሐዋርያ ፡ ቃለ ፡ ዚእሁ ፡ በም ግባር ፡ በከመ ፡ ዘከረ ፡ በመልእክቱ ፡ ዳግማዊ ፡ ኀበ ፡ ሰብእ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ፲ወ፩ዱ ፡ "ከመ ፡ ውእቱ ፡ ያረ ፡ ወተዐገሠ ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ፡ ተሞቅሐ ፡ ወቅሥፈተ ፡ ወተዘግሐ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ሞቅሕ ፡ ወሰደተ ፡ በፍርሃት ፡ ወበጻማ ፡ በድካም ፡ ወበትጋህ ፡ በረኃብ ፡ ወበጽምእ ፡ በዕርቃን ፡ ወበቍር ፡ ወበአምጣነ ፡ ዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ እንዘ ፡ ህሎ ፡ መጠውዎ ፡ ለአንበሳ" ። ወድኅረዝ ፡ ተዐገሠ ፡ ከዕወተ ፡ ደም ፡ ወነሥአ ፡ አክሊለ ፡ ስምዕ ፡ በሀገረ ፡ ሮሜ ።

፯፻፳፱ ወብዙኃን ፡ ሐዋርያት ፡ ሰማዕተ ፡ ኮኑ ፡ ወረ ሰዩ ፡ ርእሶሙ ፡ ለሰምዕ ፡ በከመ ፡ ይነግር ፡ ዜና ሆሙ ፡ ወዝንቱ ፡ ይትነበብ ፡ በዕለተ ፡ በዓ ሎሙ ። ወንስእሎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከመ ፡



በመፈወስ ፡ ከእነርሱም ፡ ሰይጣንን ፡ በማስወ ጣት ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሳፍራቸዋል ።

፯፻፳፮ ማንር ፡ ፳ ፡ በሰማዕታት ፡ በዓል ፡ የሚሰበሰቡ ትን ፡ ሰዎች ፡ የሚንቃቸው ፡ ሰው ፡ ትዕቢትን ፡ የተመላ ፡ ነውና ፡ የተወገዘ ፡ (የተለየ) ፡ ይሁን ።

፯፻፳፯ ድስቅ ፡ ፴፰ ፡ ምእመናን ፡ የክርስቶስን ፡ ሰማዕ ታት ፡ ትተው ፡ ዐላውያን ፡ ሰማዕታት ፡ ወደሚ ኗቸው ፡ ቦታ ፡ መሄድ ፡ አይገባቸውም ። ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ፍቅር ፡ መጋደላችን ፡ እንዴት ፡ መሆን ፡ እንደሚገባው ፡ እነሆ ፡ ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ ጻፈ ፡ ወደሮሜ ፡ ሰዎች ፡ በላከው ፡ መልእክቱ ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ፰ ፡ የክርስቶስን ፡ ፍቅር ፡ ማን ፡ ያስተወናል ? መከራ ፡ ነውን ? እሥራት ፡ ነውን ፡ ስደት ፡ ነውን ፡ ረኃብ ፡ ነውን ፡ መራቆት ፡ ነውን ፡ መጣላት ፡ ነውን ፡ ሰይፍ ፡ ነውን ፡ ስለአንተ ፡ ዘወትር ፡ ይገድሉ ናልና ፡ እንደሚታረዱም ፡ በጎች ፡ ሆነ ፡ ተብሎ፡ እንደተጻፈ ። በዚህ ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ የወደደንን፡ በመውደዳችን ፡ እኛ ፡ ድል ፡ እንነሣለን ፡ እኔም፡ ሊለየኝ ፡ የሚችል ፡ እንደሌለ ፡ አምናለሁ ። ሞት ፡ ቢሆን ፡ ሕይወትም ፡ ቢሆን ፡ መላእክ ት ፡ ቢሆኑ ፡ አለቆችም ፡ ቢሆኑ ፡ አሁን ፡ ያለ ውም ፡ ይመጣም ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ቢሆን ፡ ኃይለኞችም ፡ ቢሆኑ ፡ ላይኛው ፡ ቢሆን ፡ ታችኛውም ፡ ቢሆን ፡ በታች ፡ ያለው ፡ ሌላውም ፍጥረት ፡ ቢሆን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከእግ ዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ ሊለየኝ ፡ አይችልም ። (ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፴፭ - ፴፱) ።

፯፻፳፰ እነሆ ፡ ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ ለቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ በጻፈው ፡ በሁለተኛው ፡ መልእክቱ ፡ እንደተናገረው ፡ የርሱን ፡ ቃል ፡ በሥራ ፡ ጨረሰ ፲፩ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ እሥራትን ፡ ግርፋትን ፡ ከእሥር ፡ ቤት ፡ መዘጋትን ፡ መሰደድን ፡ እርሱ ፡ ታግሦ ፡ እንደተቀበለ ፡ በመፍራት ፡ በፍጹም ፡ ድካም ፡ በትጋት ፡ በመራብ ፡ በመጠማት ፡ በመ በረድ ፡ በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ሳለ ፡ ለአንበሳ ፡ ሰጡት ፡ (ጣሉት) ። ከዚህ ፡ በኋላም ፡ ደሙን ፡ አፈሰሰ ፡ በሮሜ ፡ ሀገር ፡ የሰማዕትነትን ፡ አክሊል ፡ (ክብር) ፡ ተቀበለ ። (፪ኛ ፡ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፳፱-፳፯) ።

፯፻፳፱ ብዙዎቹ ፡ ሐዋርያትም ፡ ሰማዕት ፡ ሆኑ ፡ ገድላ ቸው ፡ እንደሚናገረው ፡ ራሳቸውን ፡ ለሰማዕ ትነት ፡ አደረጉ ፡ ይኸውም ፡ (ገድላቸው) ፡ በበ ዓላቸው ፡ ቀን ፡ ይነበባል ። በእማላጅነታቸው፡

ይጸግወነ ፡ በትንብልናሆሙ ፡ ኅብረተ ፡ ወረ ድኤተ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ግብር ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት፡ ወእኰቴት ፡ እስከ ፡ ዘመነ ፡ ዘመናት ፡ አሜን ።

እንድነትን ፡ በሥራም ፡ ሁሉ ፡ ረድኤትን ፡ ይሰጠን ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንለምነው ። እስከ ፡ ዘመነ ፡ ዘመናት ፡ ድረስ ፡ ክብር ፡ ምስ ጋና ፡ ይግባው ፡ አሜን ።

---

## አንቀጽ ፡ ፳ወ፩ዱ ።

### በእንተ ፡ ድውያን ።

፯፻፹፱ ወውእቱ ፡ ፪ቱ ፡ አክፋል ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘይደሉ ፡ በእንተ ፡ ድዉያን ። ይቤ ፡ ያዕቆብ ፡ ሐዋርያ ፡ በመልእክቱ ፡ "ወአመቦ ፡ ዘይደዊ ፡ ይጸውዕ ፡ ቀሳውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከመ ፡ ይጸልዩ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወይቅብዕዎ ፡ ቅብዐ ፡ በስመ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እስመ ፡ ጸሎት ፡ በሃይማኖት ፡ ያሐይዎ ፡ ለድ ዉይ ፡ ወያነሥኦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወእመኒ ፡ ቦቱ ፡ ኃጢአት ፡ ትትኀደግ ፡ ሎቱ ።

፯፻፺ ወናሁ ፡ ስምዐ ፡ ኮነ ፡ ወንጌል ፡ ቅዱስ ፡ ከመ ፡ ለሐዋርያት ፡ ሶበ ፡ ፈነዎሙ ፡ እግዚእነ ፡ ውስተ ሀገር ፡ በጥንተ ፡ ስብከት ፡ በበ፪ቱ ፡ ኮኑ ፡ ይቀ ብዕዎሙ ፡ ለድዉያን ፡ ወይትፌወሱ ።

፯፻፺፩ ወጋኔንሂ ፡ ዘአበዮሙ ፡ ለእርድእት ፡ በጥንተ ፡ ግብሮሙ ፡ ከመ ፡ ኢይፃእ ፡ እምብእሲ ፡ ዘአዕ በዶ ፡ ወእብጽሕዎ ፡ ኀበ ፡ እግዚእነ ፡ ከመ ፡ ይፈውሶ ፡ ይቤ ፡ እግዚእ ፡ በእንቲአሁ ፡ እስመ ፡ ለዝንቱ ፡ ዘመድ ፡ ኢይክሉ ፡ አውፅኦቶ ፡ ዘእን በለ ፡ በጾም ፡ ወበጸሎት ።

፯፻፺፪ ወዳዊትኒ ፡ ነቢይ ፡ ይቤ ፡ በመጽሐፈ ፡ መዝ ሙር" ፡ ብፁዕ ፡ ዘይሌቡ ፡ ላዕለ ፡ ነዳይ ፡ ወምስ ኪን ፡ ይረድኦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዕለ ፡ ዓራተ ፡ ምስካቡ ፡ ወይዌልጥ ፡ ደዌያቲሁ ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ ውእቱ ፡ ላዕለ ፡ ዓራተ ፡ ሕማሙ" ።

፯፻፺፫ ወመጽሐፈ ፡ ነገሥትኒ ፡ ትነግር ፡ ከመ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ዘለፎ ፡ ለዘፈነወ ፡ ይስአል ፡ እምላከ፡ አፍሮን ፡ በእንተ ፡ ደዌሁ ፡ ወእሞቶ ፡ ፍጡነ ፡ በውእቱ ፡ ጊዜ ።

## አንቀጽ ፡ ፳፩ ።

### ስለድዉያን ።

፯፻፹፱ ይኸውም ፡ ሁለት ፡ ክፍል ፡ ነው ። ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ ስለድዉያን ፡ የሚገባውን ፡ ይናገራል ። ያዕቆብ ፡ ሐዋርያ ፡ በመልእክቱ ፡ እንዲህ ፡ አለ። "የታመመ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ይጸልዩለት ፡ ዘንድ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ቅባት፡ ይቀቡት ፡ ዘንድ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቀሳውስ ተን ፡ ይጥራ ። ጸሎት ፡ በሃይማኖት ፡ ድዉዩን ፡ ያድነዋልና ፡ እግዚአብሔርም ፡ ያነሣዋል ፡ ኃጢ አትም ፡ ቢኖርበት ፡ ትሠረይለታለች ። (ያዕ ፡ ፭ ፲፬ - ፲፭) ።

፯፻፺ ጌታችን ፡ በጥንተ ፡ ስብከት ፡ ሐዋርያትን ፡ ሁለት ፡ ሁለት ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ አገር ፡ በላካ ቸው ፡ ጊዜ ፡ ድዉያኑን ፡ ይቀቡአቸውና ፡ ይድ ኑ ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ እነሆ ፡ ቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ መሰ ከረ ። (ማር ፡ ፮ ፡ ፯ - ፲፫) ።

፯፻፺፩ በቀደመ ፡ ሥራቸው ፡ ሐዋርያት ፡ አእምሮውን፡ ካሳጣው ፡ ሰው ፡ ጋኔን ፡ ማውጣት ፡ ቢያቅንፋ ቸው ፡ ያድነው ፡ ዘንድ ፡ ወደጌታችን ፡ አደረ ሱት ። ስለእርሱ ፡ ጌታ ፡ ተናገረ ። ያለጾምና ፡ ያለ ፡ ጸሎት ፡ ይህንን ፡ ዘመድ ፡ (ሰይጣን ) ማስ ወጣት ፡ አይቻላቸውምና ። (ማቴ ፡ ፲፯ ፡ ፲፯ - ፳፩) ።

፯፻፺፪ ነቢዩ ፡ ዳዊትም ፡ በመዝሙሩ ፡ መጽሐፍ ፡ በደ ኃውና ፡ በችግረኛው ፡ ላይ ፡ የሚያስተውል ፡ ሰው ፡ ብፁዕ ፡ ነው ፡ አለ ። እግዚአብሔርም ፡ በተኛበት ፡ አልጋ ፡ ሳለ ፡ ይረዳዋል ፡ እርሱ ፡ በታመመበት ፡ አልጋ ፡ ሳለ ፡ ደዌዉን ፡ ይለው ጥለታል ። ( መዝ ፡ ፵ ፡ ፩ - ፫) ።

፯፻፺፫ መጽሐፈ ፡ ነገሥትም ፡ ስለ ፡ ደዌው ፡ የአፍሮንን አምላክ ፡ ይጠይቅለት ፡ ዘንድ ፡ የላከውን ፡ (አካ ዝያስን) ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደዘለፈው ፤ በዚ ያን ፡ ጊዜም ፡ ፈጥኖ ፡ እንደገደለው ፡ ትናገራ ለች ። (፪ኛ ፡ ነገ ፡ ፩ ፡ ፪ - ፬) ።

አንቀጽ ፡ ፳፪ ።

፯፻፸፩ ወጻግምኒ ፡ ዘይደሉ ፡ ላዕለ ፡ ምእመናን ፡ በእንተ ፡ ተልእኮቶሙ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ ደወይኩ ፡ ወሐወጽክሙኒ ። ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ እማን ፡ እብለክሙ ፡ ኵሎ ፡ ዘገበርክሙ ፡ ለ፩ዱ ፡ እምእሉ ፡ አኃውየ ፡ ንኡሳን ፡ ሊተ ፡ ገበርክሙ ። ወወደሶ ፡ ለዘገብረ ፡ ዘንተ ፡ ወእውረሶ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ወዘለፎ ፡ ለዘኢገብረ ፡ ዘንተ ፡ ወእርኀቆ ፡ ይሑር ፡ ኀበ ፡ ኵነኔ ፡ ዕጹብ ።

፯፻፸፪ ወእንበረ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ምሳሌ ፡ በሳምራዊ ፡ ዘእቀሰልዎ ፡ ወወድቀ ፡ ውስተ ፡ ፍኖት ፡ ወበዘጽሕቀ ፡ በግብሩ ።

፯፻፸፫ ወሐዋርያትኒ ፡ ይቤሉ ፡ ድስቅ ፡ ወለድዉያንሂ ፡ እለ ፡ ዐጸቦሙ ፡ ደዌ ፡ ዘኢይክሉ ፡ ሐዊረ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሐውጽዎሙ ፡ እለ ፡ የእምርዎሙ ፡ ኵሎ ፡ ዕለተ ።

፯፻፸፬ ረስጣ ፡ ፵ወ፪ቱ ፡ ወዲያቆናትኒ ፡ ይንግርዎ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ በእንተ ፡ ድዉያን ፡ ከመ ፡ የሐውጾሙ ። ወተፍጻሜተ ፡ ዝንቱ ፡ ፍካሬ ፡ ህሎ ፡ በአንቀጸ ፡ ምጽዋት ።

ስለ ፡ ሙታን ።

፯፻፸፩ ጻግመኛም ፡ ስለአገልግሎታቸው ፡ ለምእመናን ፡ የሚገባው ፡ ነው ፡ ጌታችን ፡ ብታመም ፡ ጠየቃችሁኝ ፡ አለ ። (ማቴ ፡ ፳፭ ፡ ፴፮) ። ጻግመኛም ፡ ከእነዚህ ፡ ከታናናሾቹ ፡ ወንድሞቼ ፡ ወገን ፡ ለአንዱ ፡ ያደረጋችሁት ፡ ለእኔ ፡ ማድረጋችሁ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ በእውነት ፡ እነግራችኋለሁ ፡ አለ ።(ማቴ ፡ ፳፭ ፡ ፵) ። ይህን ፡ ያደረገውን ፡ አመስግነው ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትንም ፡ አወረሰው ። ይህን ፡ ያላደረገውን ፡ ግን ፡ ዘለፈው ፡ ጭንቅም ፡ ወደሚሆን ፡ ቅጣት ፡ ይሄድ ዘንድ ፡ አራቀው ።

፯፻፸፪ ስለዚህም ፡ ወንበዴዎች ፡ ያቆሰሉትን ፡ በጐዳና ፡ የወደቀውን ፡ ሰው ፡ ለመርዳት ፡ በተጋ ፡ በሳምራዊ ፡ ምሳሌ ፡ ጻፈ ። (ሉቃ ፡ ፲ ፡ ፴፫ - ፴፯)

፯፻፸፫ ሐዋርያትም ፡ ተናገሩ ፡ እንዲህም ፡ አሉ ። ድስቅ ፡ ወደቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሄድ ፡ የማይቻላቸውን ፡ ደዌ ፡ ያስጨነቃቸውን ፡ ድውያንንም፡ የሚያውቋቸው ፡ ዘወትር ፡ ይጠይቋቸው ።

፯፻፸፬ ረስጣ ፡ ፵፪ ፡ ዲያቆናቱም ይጠይቋቸው ፡ ዘንድ፡ ስለታመሙት ፡ ሰዎች ፡ ለኤጲስ ቆጶሱ ፡ ይንገሩት ። የዚህ ፡ ትርጓሜ ፡ መጨረሻ ፡ በአንቀጸ፡ ምጽዋት ፡ አለ ። (ፍ ፡ ነ ፡ ፲፯ ፡ ፮፻፴፭) ።

## አንቀጽ ፡ ፳ወ፪ቱ ።

በእንተ ፡ ሙታን ።

፯፻፸፭ ድስቅ ፡ ፴ወ፩ቱ ፡ ተጋብኡ ፡ ዘእንበለ ፡ ህኬት ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወእንብቡ ፡ መጻሕፍተ ፡ ቅዱሳተ ፡ ወዘምሩ ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ኖሙ፡ እምነ ፡ ሰማዕታት ፡ ወቅዱሳን ፡ ቀዳማውያን ፡ ወአኃዊክሙ ፡ እለ ፡ ኖሙ ፡ ወእሙንቱ ፡ ምእመናን ፡ በእግዚእነ ፡ ወአዕርጉ ፡ ሎሙ ፡ አኰቴተ ፡ ቍርባን ፡ ዘውእቱ ፡ ሥጋሁ ፡ ቅዱስ ፡ ወደሙ ፡ ክቡር ፡ ለንጉሥ ፡ ሰማያዊ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያናቲክሙ ። ወበእንተ ፡ ተሰናእሎቱ ፡ ለዘኖመ ፡ ወተጋንዩ ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ኖሙ ፡ እንዘ ፡ ተሐውሩ ፡ቅድሜሆሙ ፡ እንዘ ፡ ትዜምሩ ።

፯፻፸፮ ወእመ ፡ ኮነ ፡ ምእመነ ፡ በክርስቶስ ፡ ይቤ ፡ ዳዊት ፡ ነቢይ ፡ ክቡር ፡ ሞቶሙ ፡ ለጻድቃኒሁ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ። ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ግብኢ ፡ ነፍስየ ፡ ውስተ ፡ ዕረፍትኪ ፡ እስመ ፡

## አንቀጽ ፡ ፳፪ ።

ስለሙታን ።

፯፻፸፭ ድስቅ ፡ ፴፩ ፡ ያለስንፍና ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተሰብሰቡ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትንም ፡ አንብቡ ፡ ከሰማዕታት ፡ ደጋግ ፡ ከሆኑ ፡ ከቅዱሳን ፡ ወገን ፡ ስለሞቱት ፡ ስለሞቱ ፡ ወንድሞቻችሁም አመስግኑ ፡ (ዳዊት ፡ ድገሙ) ፡ እነዚህም ፡ በጌታችን ፡ ያመኑ ፡ ምእመናን ፡ ናቸው ። በቤተ፡ ክርስቲያናችሁ ፡ መሥዋዕት ፡ ሠዉላቸው ፡ ይኸውም ፡ የሰማያዊ ፡ ንጉሥ ፡ ቅዱስ ፡ ሥጋውና ፡ ክቡር ፡ ደሙ ፡ ነው ። የሞተውን ፡ ሰው ፡ ስለመሰናበት ፡ በፊታቸው ፡ እየሄዳችሁ ፡ እያመሰገናችሁ ፡ ስለሞቱት ፡ ሰዎች ፡ ጸልዩ ።

፯፻፸፮ በክርስቶስ ፡ ያመነ ፡ ከሆነ ፡ ነቢዩ ፡ ዳዊት ፡ የጻድቃን ፡ ሞት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክቡር ፡ ነው ፡ አለ ። (መዝ ፡ ፻፲፭ ፡ ፮) ። ዳግመኛም ፡ ነፍሴ ፡ (ሰውነቴ) ፡ ወደዕረፍትሽ ፡ ግቢ ፡ እግዚ

እግዚአብሔር ፡ አሠነየ ፡ ለኪ ።

፯፻፹ ወእለሰ ፡ እምኑ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እልቦ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ሞት ፡ በከመ ፡ ይቤሎሙ ፡ እግዚእነ ፡ ለሰዱቃውያን ።

፯፻፹፩ እስመ ፡ እዕፅምቲሆሙ ፡ ለሕያዋን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኢኮነ ፡ ምኑነ ፡ ወኢርኩሰ ፡ እስመ ፡ ኤልሳዕ ፡ ነቢይ ፡ እምድኅረ ፡ ሞቱ ፡ እንሥአ ፡ ምዉተ ፡ ዘቀተልዎ ፡ ሠራዊተ ፡ ሶርያ ፡ ሶበ ፡ ቀርበ ፡ ሥጋሁ ፡ ኀበ ፡ እዕፅምተ ፡ ኤልሳዕ ፡ ሐይወ ፡ ወተንሥአ ፡ ወኢኮነ ፡ ዝንቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ሶበ ፡ ኮነ ፡ ሥጋሁ ፡ ለኤልሳዕ ፡ ቅዱስ ፡ ወንጹሐ ።

፯፻፹፪ ወካዕበ ፡ ዮሴፍ ፡ ጠቢብ ፡ ኮነ ፡ የሐቅፎ ፡ ለሥጋ ፡ ያዕቆብ ፡ አቡሁ ፡ ላዕለ ፡ ዓራቱ ፡ እምድኅረ ፡ ሞቱ ። ወሙሴኒ ፡ ወኢያሱ ፡ ኮኑ ፡ ይፀውሩ ፡ ሥጋሁ ፡ ለዮሴፍ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ወኢተኈለቈ ፡ ቦሙ ፡ አበሳ ። ወንሕነኒ ፡ ካዕበ ፡ አ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ወሕዝባውያን ፡ ለንግሥሥ፡ በድነ ፡ እለ ፡ ኖሙ ፡ በተዓቅቦ ፡ ወኢትትሐዘቡ ፡ ክመ ፡ አንትሙ ፡ ትረክሱ ፡ በዝንቱ ፡ ወኢትመንኑ ፡ እዕፅምቲሆሙ ፡ በዝንቱ ፡ ምክንያት ።

፯፻፹፫ ነበረ ፡ በቀኖና ፡ ዘተጽሕፈ ፡ ለንገሥት ፡ ሶበ ፡ ሞተት ፡ ብእሲት ፡ በወሊድ ፡ አው ፡ በመዋዕለ ፡ ሕርሳ ፡ ይሕፅብዋ ፡ ወይግንዝዋ ፡ በካልእ ፡ ልብስ ፡ ዘኢወለደት ፡ ቦቱ ፡ ወይጸልዩ ፡ ላዕሌሃ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እስመ ፡ ሞት ፡ አንጽሓ ።

፯፻፹፬ ወሐዊበ ፡ ምዉት ፡ እምቅድመ ፡ ይግንዝዎ ፡ ድልው ፡ ውእቱ ፡ ወእኮ ፡ ፈጠራ ፡ እስመ ፡ መጽሐፈ ፡ አብረክሲስ ፡ ይነግር ፡ ከመ ፡ ለጣቢታ ፡ ረድእት ፡ ዘአንሥአ ፡ ጴጥሮስ ፡ እምድኅረ ፡ ሞተት ፡ ሐፀብዋ ፡ ወእመሰ ፡ ኮነ ፡ ዝንቱ ፡ ዘኢይደሉ ፡ እምኢገብርዎ ፡ ምእመናን ፡ በመዋዕለ ፡ አርድእት ፡ እሙንቱኒ ፡ ኢከልእዎሙ ፡ ካዕበ ።

፯፻፹፭ ወዓዲ ፡ ይከውኑ ፡ ሙታን ፡ ርሱሓነ ፡ በእሠረ ፡ ደዌሆሙ ፡ ወይደሉ ፡ ከመ ፡ ኢያብእዎሙ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንበለ ፡ ይሕፅብዎሙ ።

፯፻፹፮ ዘ፩ቱ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ መዋቲ ፡ ካህነ ፡ ይኩን ፡ ቅድመ ፡ ምሥዋዕ ፡ እምላካዊ ። ወለእመሰ ፡



እብሔር ፡ አዘጋጅቶልሻልና ። (መዝ ፡ ፺፲፩ ፡ ፺)።

፯፻፹ በእግዚአብሔር ፡ ያመኑ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ጌታችን ፡ ለሰዱቃውያን ፡ እንደነገራቸው ፡ ሞት ፡ የለባቸውም ። (ማቴ ፡ ፳፪ ፡ ፴ - ፴፪) ።

፯፻፹፩ የሞቱ ፡ ሰዎች ፡ አጥንት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የተናቀና ፡ የረከሰ ፡ አይደለም ፡ እኮ ። ነቢዩ ፡ ኤልሳዕ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የሦርያ ፡ ወታደሮች ፡ የገደሉትን ፡ ሙት ፡ አስነሥቷልና ፡ ሥጋው ፡ ወደኤልሳዕ ፡ አጽም ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ድኖ ፡ ተነሣ ፡ የኤልሳዕ ፡ ሥጋ ፡ ንጹሕና ፡ ቅዱስ ባይሆን ፡ ኑሮ ፡ ይህ ፡ ባልሆነም ፡ ነበር ። (፪ኛ ፡ ነገ ፡ ፲፫ ፡ ፪ - ፳፪) ።

፯፻፹፪ ዳግመኛም ፡ ብልሁ ፡ ዮሴፍ ፡ አባቱ ፡ ያዕቆብ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ሥጋውን ፡ በአልጋው ፡ ላይ ፡ ያቅፈው ፡ ነበር ። (ዘፍ ፡ ፶ ፡ ፩ - ፪) ። ሙሴና ፡ ኢያሱም ፡ የዮሴፍን ፡ አጥንት ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ይሸከሙ ፡ ነበር ፡ በደልም ፡ ሁኖ ፡ አልተቆጠረባቸውም ። (ዘፀ ፡ ፲፫ ፡ ፲፱) ። ዳግመኛም ፡ ኤጲስቆጶሳትና ፡ ሕዝባውያን ፡ ሆይ ፡ እኛም ፡ በተዐቅቦ ፡ የሞቱትን ፡ ሰዎች ፡ በድን ፡ እንዳስ ። በዚህ ፡ እናንተ ፡ እንደምትረክሱ ፡ አትጠራጠሩ ፡ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ሬሳቸውን ፡ አትናቁ ።

፯፻፹፫ ለንገሥታት ፡ በተጻፈው ፡ መጽሐፍ ፡ ተጻፈ ፡ ሴት ፡ በወሊድ ፡ ወይም ፡ በአራስነቷ ፡ ወራት ፡ በሞተች ፡ ጊዜ ፡ አጥበው ፡ ባልወለደችበት ፡ በሌላ ፡ ልብስ ፡ ይገንዟት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ይጸልዩላት ፡ ሞት ፡ አንጽቷታልና ።

፯፻፹፬ ከመገነዛቸውም ፡ በፊት ፡ ሙቱን ፡ ማጠብ፡ የተገባ ፡ ነው ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ አይደለም ፡ ጴጥሮስ ፡ ያስነሣትን ፡ አገልጋይቱን ፡ ጣቢታን ፡ ከሞተች ፡ በኋላ ፡ እንዳጠቧት ፡ የሐዋርያት ፡ ሥራ ፡ ይናገራልና ፡ ይህስ ፡ የማይገባ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ በሐዋርያት ፡ ዘመን ፡ ምእመናን ፡ ባልሠሩትም ፡ ነበር ፡ እነርሱም ፡ ዳግመኛ ፡ እልከለከሏቸውም ። (የሐዋ ፡ ፱ ፡ ፴፯) ።

፯፻፹፭ ዳግመኛም ፡ ሙታን ፡ በደዌያቸው ፡ ጸናት ፡ ርሱሓን ፡ ይሆናሉ ፡ ሳያጥቡ ፡ ወደቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሊያገቧቸው ፡ አይገባም ።

፯፻፹፮ ፩ ፡ ሟቹ ፡ ካህን ፡ ቢሆን ፡ እምላካዊ ፡ በሆነ ፡ በመንበሩ ፡ ፊት ፡ (በመቅደስ) ፡ ይሁን ። ከሕ

ኮነ ፡ እምነ ፡ ሕዝብ ፡ ይኩን ፡ ታሕተ ፡ ምሥዋዕ ። ወእምድኅረዝ ፡ ይዕጥን ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ በጸሎት ፡ ኅበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወበአኰቴት ፡ ሎቱ ።

፮፻፹፯ ወእምድኅሬሁ ፡ ያንብቡ ፡ ላእካን ፡ እምቃላተ ፡ መዝሙር ፡ ወእምተስፋት ፡ ጽዱቃት ፡ በእንተ፡ ትንሣኤን ፡ ዘግኑሥ ፡ እምነ ፡ ሐሰት ፡ ወበእንተ ፡ ተእምኖ ፡ መሥመሪት ።

፮፻፹፰ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ይቅድም ፡ ሊቀ ፡ ካህናት፡ ወይጸሊ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወእምድኅረ ፡ ፍጻሜ ፡ ጸሎቱ ፡ ይሰዐሞ ፡ እንዘ ፡ ይሰነእሎ ፡ ወእምድኅሬሁ ፡ ይሰዐምዎ ፡ ጉባኤ ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡ ሀየ ። ወእምድኅረዝ ፡ ይከዐው ፡ ላዕሌሁ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ቅብዐ ፡ ዘይት ፡ ወይጸሊ ፡ በአንቲአሁ ፡ ጸሎተ ፡ ክሡተ ።

፮፻፹፱ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ያንብርዎ ፡ ለሥጋሁ ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ ክቡር ፡ በእማዋረ ፡ ሥጋ ፡ ንጹሕ ፡ ዘስንእው ፡ ምስሌሁ ፡ ውስተ ፡ መዓርጉ ።

፮፻፺ ረስጣ ፡ ፎ ፡ ወግበሩ ፡ በሣልስት ፡ ዕለት ፡ ተዝካረ ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ኖሙ ፡ በመዝሙራት ፡ ወጸሎታት ፡ በእንተ ፡ ዘተንሥአ ፡ በሣልስት ፡ ዕለት ።

፮፻፺፩ ወግበሩ ፡ በሳብዕት ፡ ዕለት ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለሕያዋን ፡ ወለምዉታን ።

፮፻፺፪ ወግበሩ ፡ ካዕበ ፡ በፍጻሜ ፡ ወርኅ ፡ በአምሳለ ፡ ቀዳማውያን ፡ ከማሁ ፡ ኀዘኑ ፡ ሕዝብ ፡ በእንተ ፡ ሙሴ ። ወግበሩ ፡ ካዕበ ፡ በፍጻሜ ፡ ዓመት ፡ በአምሳለ ፡ ተዝካሮሙ ፡ ወሀቡ ፡ ለነዳያን ፡ እምጥሪቱ ፡ ለዘሞተ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ተዝካረ ፡ ሎቱ ፡ ወስበ ፡ ተጸዋዕክሙ ፡ በውእቱ ፡ ዕለት ፡ ብልዑ ፡ በሥርዓት ፡ ወበፍርሃተ ፡ እግዚአብሔር

፮፻፺፫ በስ ፡ ፊወ፩ዱ ፡ ወይደሉ ፡ ከመ ፡ ያዕርጉ ፡ ቍርባነ ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ሞቱ ፡ በሣልስት ፡ ዕለት ፡ ወበሳብዕት ። ወበ፲ወ፩ቱ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እሐቲ ፡ ጉባኤ ።

፮፻፺፬ ጴጥ ፡ ወበታስዕት ፡ ዕለት ። ወበ፲ወ፪ቱ ፡ ዕለት። ወከማሁ ፡ በ፴ ፡ ዕለት ። ወበተፍጻሚተ ፡ ፪ቱ ፡ አውራኅ ።

፮፻፺፭ ወዘተሠርዐ ፡ ይእዜ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ እዕርጎ ፡ ቍርባን ፡ በዕለተ ፡ ተቀብረ ፡ ወበተፍ



ዝቡ ፡ ወገን ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ከመቅደስ ፡ ውጭ ፡ ይሁን ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ እየጸለየ ፡ እርሱንም ፡ በማመስገን ፡ ይጠን ።

፮፻፹፯ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ልዑካኑ ፡ ከመዝሙር ፡ ቃላት፡ ከሐሰት ፡ የራቀ ፡ ስለትንሣኤ ፡ ከሚናገር ፡ ከእውነተኛው ፡ ተስፋ ፡ ወገን ፡ ደስ ፡ ስለምታሰኘው ፡ እምነት ፡ ያንብቡ ፡ (ይስበኩ) ።

፮፻፹፰ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ አስቀድሞ ፡ ይጸልይለት ፡ ጸሎቱንም ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ ሲሰናበት ፡ ይሳመው፡ ከርሱም ፡ ቀጥሎ ፡ ከዚያ ፡ ያሉት ፡ የተሰበሰቡት ፡ ይሳሙት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ የዘይቱን ፡ ቅባት፡ ያፍስስበት ፡ ስለርሱም ፡ የታወቀውን ፡ ጸሎት ፡ ይጸልይ ።

፮፻፹፱ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በመዓርግ ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ የሚተካከል ፡ የቅዱስ ፡ ሰው ፡ ሬሳ ፡ በተቀበረበት ፡ በከበረ ፡ ቦታ ፡ ሥጋውን ፡ ይቅበሩት ።

፮፻፺ ረስጣ ፡ ፎ ፡ ጌታ ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ስለተነሣ ፡ ስለሞቱ ፡ ሰዎች ፡ በመዝሙርና ፡ በጸሎት ፡ በሣልስቱ ፡ መታሰቢያቸውን ፡ አድርጉ ።

፮፻፺፩ የሕያዋንንና ፡ የሙታንን ፡ መታሰቢያ ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ አድርጉ ።

፮፻፺፪ ዳግመኛም ፡ በቀደሙት ፡ ሰዎች ፡ አምሳል ፡ በወሩ ፡ መጨረሻ ፡ አድርጉ ። ሕዝቡ ፡ ስለሙሴ ፡ እንደዚሁ ፡ አዘኑ ። ዳግመኛም ፡ በመታሰቢያቸው ፡ አምሳል ፡ በዓመቱ ፡ መጨረሻ ፡ አድርጉ ፡ ከሞተውም ፡ ሰው ፡ ገንዘብ ፡ ለነዳያን ፡ ስጡ ፡ መታሰቢያ ፡ ይሆንለት ፡ ዘንድ ፡ በዚያን ፡ ቀን ፡ ብትጠሩ ፡ በሥርዓትና ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመፍራት ፡ ብሉ ።

፮፻፺፫ በበ ፡ ፊ፩ ፡ ስለሞቱ ፡ ሰዎች ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ ቍርባን ፡ ሊያስቆርቡ ፡ ይገባል ። በ፲፩ኛው ፡ ቀን ፡ እንዲት ፡ መሰብሰቢያ ፡ በምትሆን ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቍርባን ፡ ያስቁርቡ ።

፮፻፺፬ ጴጥ ፡ በዘጠኘኛው ፡ ቀን ፡ በ፲፪ኛውም ፡ ቀን ፡ እንዲሁም ፡ በአርብዓኛው ፡ ቀን ፡ በሁለት ፡ ወር ፡ መጨረሻም ።

፮፻፺፭ በአኛ ፡ ቤተክርስቲያን ፡ የታዘዘም ፡ በተቀበረበት ፡ ቀን ፡ ቍርባን ፡ ማስቁረብ ፡ ነው ፡ በስድ

ጸሚተ ፡ ወርኅ ፡ ወበተፍጻሜተ ፡ ፲ቱ ፡ አው ራኅ ፡ ወበተፍጸሜተ ፡ ዓመት ። ወፈድፋደሰ ፡ እመ ፡ ተክህሎሙ ፡ ያዕርጉ ፡ ቍርባናተ ፡ ፴ ፡ ዕለተ ፡ እምዕለተ ፡ ተቀብረ ፡ ወየሀቡ ፡ ለነዳያን ወዘወሰከ ፡ ላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ ሎቱኒ ፡ ወለዘሞተኒ ፡ ይፈድፋድ ፡ ዓስቦሙ ፡ በአምጣነ ፡ ጸሕቁ ፡ ወፍ ሥሓሁ ፡ ለምዉት ፡ ይከውን ፡ በዝንቱ ።

፻፶፮ ዘኒቅያ ፡ ፳ወ፱ቱ ፡ ወለእመ ፡ ሞተ ፡ ፩ዱ ፡ ኤጲስ ቆጶስ ፡ እምኤጲስቆጶሳት ፡ ይሑሩ ፡ ሊቀ ፡ ካህ ናት ፡ ወሊቀ ፡ ዲያቆናት ፡ ቅድመ ፡ ዓራተ ፡ ግን ዘቱ ፡ በከመ ፡ የሐውሩ ፡ ደቂቅ ፡ ቅድመ ፡ ግን ዘተ ፡ አቡሆሙ ። ወእመ ፡ ሞተ ፡ ፩ዱ ፡ እም እሉ ፡ ይሑር ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ቅድመ ፡ ዓራተ ፡ ግንዘቱ ፡ በከመ ፡ የሐውር ፡ አብ ፡ ቅድመ ፡ ግን ዘተ ፡ ውሉዱ ። ወያንብብ ፡ በግንዘተ ፡ እሉ ፡ እምነ ፡ ጸሎታት ፡ በከመ ፡ ይደልዎሙ ፡ ለመ ምሀራን ፡ ወለአበው ፡ ኄራን ፡ መንፈሳውያን ፡ ወየሀልዉ ፡ በጊዜ ፡ ግንዘቶሙ ፡ ኵሎሙ ፡ መር ዔት እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ኮኑ ፡ ይሰመዩ ፡ አበወ ፡ ለኵሎሙ ።

፻፶፯ ወይሰዱ ፡ መባአ ፡ በዕለተ ፡ ሞቶሙ ፡ ለኵሉ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ወምኔታት ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡ ውስተ ፡ ውእቱ ፡ መካን ፡ ከመ ፡ ይዝከ ርዎሙ ፡ ወዝንቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ግዘት ።

፻፶፰ ረስጣ ፡ ፺ወ፺ቱ ፡ ወኢይትአንተል ፡ ፩ዱሂ ፡ በእንተ ፡ መቃብሩ ፡ ለሰብእ ፡ አላ ፡ የሀብ ፡ ዓስ በሙ ፡ ለእለ ፡ ይከርዩ ፡ ወየዐቅቡ ፡ ውእተ ፡ መካነ ፡ በጽሕቅ ፡ ወይሴስዮሙ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እምዘ ፡ ይትወሀብ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ።

፻፶፱ ዘተሰሎንቄ ፡ ዘ፲ወ፫ቱ ፡ ወኢይደልወነ ፡ ከመ ፡ ንኅዝን ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ኖሙ ፡ ከመ ፡ ኵሎሙ ፡ አሕዛብ ፡ እለ ፡ አልቦሙ ፡ ተስፋ ።

፻፷ ዘቆሮንቶስ ፡ ፯ቱ ፡ እስመ ፡ ኀዘን ፡ ዘይከውን ፡ በእንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያረብኅ ፡ ንስሓሁ ፡ ለሕይወት ፡ ወኀዘንኒ ፡ ዘይከውን ፡ በእንተ ፡ ዓለም ፡ ያረብኅ ፡ ሞተ ።

፻፷፩ በስ ፡ ፶ወ፳ቱ ፡ መጅ ፡ ፺ ፡ ወለካህን ፡ ለእመ ፡ ሞተ ፡ ፩ዱ ፡ እምአዝማዲሁ ፡ ኢይተከዝ ፡ ላዕ ሌሁ ፡ ከመ ፡ ተረፈ ፡ አሕዛብ ፡ ወኢይስጥጥ ፡ አልባሲሁ ፡ ወኢያዝልፍ ፡ ብካየ ፡ ወኢይንጺ ፡ ሥዕርተ ፡ ርእሱ ፡ አላ ፡ ያእኵቶ ፡ ለእግዚአብ ሔር ፡ ብዙኀ ፡ ወይኩን ፡ ተዓጋሜ ፡ በመከራሁ ፡



ስት ፡ ወርና ፡ በዓመቱም ፡ መጨረሻ ፡ ይልቁ ንም ፡ ቢቻላቸው ፡ ከተቀበረበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ቍርባን ፡ ያስቆርቡ ፡ ለነዳያንም ፡ ይስጡ ፡ በዚህም ፡ ላይ ፡ የጨመረ ፡ እንደ ትጋቱ፡ መጠን ፡ የእርሱም ፡ የሟቹም ፡ ዋጋቸው ፡ ይበ ዛል ፡ የሟቹም ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ በዚህ ፡ ይሆ ናል ።

፻፶፮ ኒቅያ ፡ ፳፱ ፡ ከኤጲስቆጶሳቱ ፡ ወገን ፡ አንዱ ፡ ኤጲ ስቆጶስ ፡ ቢሞት ፡ ልጆች ፡ በአባታቸው ፡ ሬሳ ፡ ፊት እንደሚሄዱ ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱና ፡ ሊቀ ፡ ዲያቆኑ ፡ ሬሳው ፡ ባለበት ፡ አልጋ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ይሂዱ ። ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ ቢሞት ፡ አባት ፡ በልጁ ፡ አስ ከሬን ፡ ፊት ፡ እንደሚሄድ ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ በአ ስከሬኑ ፡ ፊት ፡ ይሂድ ። እነዚህ ፡ በሚገነዙ በት ፡ ጊዜ ፡ ከጸሎት ፡ ወገን ፡ ለመምህራንና ፡ መንፈሳውያንም ፡ ለሆኑት ፡ ለደጋጉ ፡ አባቶች ፡ እንደሚገባቸው ፡ ያንብብ ፡ (ይድገም) ። ግንዘ ታቸው ፡ በሚደገምበትም ፡ ጊዜ ፡ ምእመናን ፡ ሁሉ ፡ ይገኙ ፡ (ይኑሩ) ፡ እነርሱ ፡ የሁሉ ፡ አባ ቶች ፡ ይባላሉና ።

፻፶፯ በጸሎት ፡ ያስቢቻው ፡ ዘንድ ፡ በዚያ ፡ ቦታ ፡ ላሉት ፡ ገዳማትና ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ሁሉ ፡ በሞቱበት ፡ ቀን ፡ መባእ ፡ ይውሰዱ ፡ ይኸውም ፡ ያልተወገዘበት ፡ ነው ።

፻፶፰ ረስጣ ፡ ፺፺ ፡ አንዱስ ፡ እንኳ ፡ ስለሰው ፡ መቃ ብር ፡ ቸል ፡ አይበል ፡ መቃብሩን ፡ ለሚቆፍ ሩና ፡ ያነን ፡ ቦታ ፡ (መቃብሩን) ፡ በትጋት ፡ ለሚጠብቁ ፡ ሰዎች ፡ ዋጋቸውን ፡ ይስጣቸው ፡ እንጂ ። ኤጲስቆጶሱም ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሚሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ይመግባቸው ።

፻፶፱ ተሰሎንቄ ፡ ፲፫ ፡ ተስፋ ፡ እንደሌላቸው ፡ እንደ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ስለሞቱ ፡ ሰዎች ፡ ልናዝን ፡ አይገባንም ። (፩ኛ ፡ ተሰ ፡ ፬ ፡ ፲፫) ።

፻፷ ቆሮንቶስ ፡ ፯ ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ የሚሆን ፡ ኀዘን ፡ ፍጻሜው ፡ ሕይወትን ፡ ያበዛል ፡ ስለዓለ ሙም ፡ የሚሆን ፡ ኀዘን ፡ ሞትን ፡ ያበዛልና ። (፪ኛ ፡ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፲) ።

፻፷፩ በስ ፡ ፶፳ ፡ መጅ ፡ ፺ ፡ ካህን ፡ ከዘመዶቹ ፡ ወገን ፡ አንዱ ፡ ቢሞት ፡ እንደቀሩት ፡ አሕዛብ፡ አይዘን ፡ ልብሱንም ፡ አይቅደድ ፡ ልቅሶን ፡ አያ ዘውትር ፡ የራስ ፡ ጠጉሩን ፡ አይንጭ ፡ እግዚአ ብሔርን ፡ ፈጽሞ ፡ ያመስግነው ፡ እንጂ ። በመ ከራውም ፡ እንደ ፡ ጻድቁ ፡ እንደ ፡ ኢዮብ ፡ ትዕ

አንቀጽ ፡ ፳፱ ።

ከመ ፡ ኢዮብ ፡ ጻድቅ ።
ተፈጸመ ፡ ክፍል ፡ ቀዳማዊ ፡ ዘውእቱ ፡ ሕግ ፡ መንፈሳዊ ፡ ወለእግዚእነ ፡ አኰቴት ፡ ወክብር ፡ ወእምኔሁ ፡ ንስእል ፡ ረድኤተ ፡ ወጥዒና ፡ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እስከ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

ስለ ፡ ሙታን ።

ግሥተኛ ፡ ይሁን ።
መጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ ተፈጸመ ። ይኸውም ፡ መንፈሳዊ ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ ለጌታችን ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ። ከርሱም ፡ ዘንድ ፡ ረድኤትንና ፡ ጤናን ፡ እንለምን ።
ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ። እስከ ፡ ዘለዓለሙ ፡ አሜን ።

በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ዱ ፡ አምላክ ፡ ክፍል ፡ ዳግማዊ ፡ በእንተ ፡ ምግባራት ፡ እንተ ፡ ይሜግቡ ፡ ባቲ ፡ ወእንተ ፡ ይፈልጥዋ ፡ ወእንተ ፡ ይከልሉ ፡ ኪያሃ ፡ ወበእንተ ፡ ማኅደር ፡ ወናሁ ፡ አቅደምነ ፡ ፈሊጠ ፡ አናቅጺሁ ፡ በክፍል ፡ ቀዳማዊ ።

## አንቀጽ ፡ ፳ወ፫ቱ ።

በእንተ ፡ መብልዕ ፡ ወአልባስ ፡ ወማኅደር ፡ ወተግባረ ፡ እድ ፡ ዘይደሉ ፡ ለመሢሐውያን ።

፷፻፪ ወመብልዕሰ ፡ በውስተ ፡ ሕግ ፡ መሢሐዊት ፡ አልቦ ፡ ውስቴቱ ፡ ሕርመት ፡ ዘእንበለ ፡ ዘከልኡ ፡ ሐዋርያት ፡ እምኔሁ ፡ በመጽሐፈ ፡ አብረክሲስ ፡ ወበቀኖናሆሙ ፡ በብሂሎቶሙ ፡ ናሁ ፡ ሠምረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወሠመርነ ፡ ንሕነኒ ፡ ካዕበ ፡ ከመ ፡ ኢናንብር ፡ ላዕሌክሙ ፡ ፆረ ፡ ክቡደ ፡ ዘይፈደፍድ ፡ ዘእንበለ ፡ ዝንቱ ፡ ዘተኀድጉ ፡ ኪያሁ ፡ በግብር ፡ ወውእቱ ፡ ከመ ፡ ትርኅቁ ፡ እምበሊዐ ፡ ደም ፡ ወሕንቅ ፡ ወመሥዋዕት ፡ ጣዖት ፡ ወብላዐ ፡ እርዌ ።

፷፻፫ ወለእሉሂ ፡ የሐርምዎሙ ፡ በእንተ ፡ ዘሀሎ ፡ ውሰቴቶሙ ፡ እምሕማም ፡ ነፍሳዊ ። እስመ ፡ ተሰናእዎ ፡ ምስለ ፡ መምለኪያነ ፡ ጣዖት ፡ በበሊዐ ፡ ዘይዘብሕዎ ፡ ለአማልክት ፡ ይከውን ፡ ዘይሳተፎሙ ፡ በአምልኮቶሙ ፡ ወይስሕቦ ፡ ዝንቱ ፡ ኀበ ፡ አምልኮ ፡ ጣዖታት ። ወበእንተ ፡ ዘሀሎ ፡ ውስቴቱ ፡ እምሕማም ፡ ሥጋዊ ፡ ወነፍሳዊ ፡ እስመ ፡ ይእቲ ፡ ታማስን ፡ ቱስሕተ ፡ ሥጋ ፡ ማስኖ ፡ ዘያበጽሕ ፡ ኀበ ፡ ሙስና ፡ ፍጥረት ፡ ወዓዲ ፡ ትወስድ ፡ ኀበ ፡ ሀጕለ ፡ አባል ።

፷፻፬ ወእኮ ፡ ዘአሕረምዋ ፡ እስመ ፡ ርኩስት ፡ ይእቲ ፡ በፍጥረታ ፡ እስመ ፡ እምፍጥረተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይእቲ ። ወናሁ ፡ ተጽሕፈ ፡ ለነ ፡ በውስተ ፡ አሪት ፡ ዘይብል ፡ "ወርእየ ፡ እግዚአብሔር ፡

በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ አንድ ፡ አምላክ ። ሁለተኛ ክፍል ። ስለ ፡ ምግባራት ፡ ለይተው ፡ ስለሚያስተዳድሩባትና ፡ እርሷንም ፡ ስለሚከለክሉባት ፡ ስለቤትም አሠራር፡ ይናገራል ። እነሆ ፡ አንቀጾችን ፡ በመጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ ለይተን ፡ ተናግረናል ።

## አንቀጽ ፡ ፳፫ ።

ስለ ፡ መብልና ፡ ስለ ፡ ልብስ ፡ ስለ ፡ ቤትም ፡ ለክርስቲያኖች ፡ ስለሚገባው ፡ የእጅ ፡ ሥራ ።

፷፻፪ ሐዋርያት ፡ በግብረ ፡ ሐዋርያትና ፡ በሲኖዶሳቸው ፡ በግድ ፡ ከምትተዉት ፡ ከዚህ ፡ በቀር ፡ የበለጠ ፡ ከባድ ፡ ሸክም ፡ በላያችሁ ፡ እንዳናኖር ፡ እነሆ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፈቅዷል ፡ እኛም ፡ ደግሞ ፡ ፈቀድን ፡ ብለው ፡ ከከለከሉት ፡ በቀር ፡ በክርስቶስ ፡ ሕግ ፡ የሚከለከል ፡ መብል የለም ። (የሐዋ ፡ ፲፭ ፡ ፳፯ - ፳፱) ። ይኸውም ፡ ደምን ፡ ታንቆ ፡ የሞተውን ፡ ለጣዖት ፡ የተሠዋውን ፡ አውሬ ፡ የነከሰውን ፡ ከመብላት ፡ ትከለከሉ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

፷፻፫ እኒህንም ፡ የሚከለክሏቸው ፡ በውስጣቸው ፡ ነፍስን ፡ (ሰውነትን) ፡ የሚጎዳ ፡ ሕማም ፡ ስላለ ፡ ነው ። ለጣዖታት ፡ የተሠዋውን ፡ በመብላት ፡ ጣዖትን ፡ ከሚያመልኩ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ መሆን ፡ በአምልኮታቸው ፡ አንድ ፡ የሚያደርጋቸው ፡ ይሆናልና ። ይህም ፡ ጣዖትን ፡ ወደ ፡ ማምለክ ፡ ይስበዋል ። ነፍስንም ፡ ሥጋንም ፡ የሚጎዳ ፡ ሕማም ፡ በውስጡ ፡ ስላለ ፡ ነው ። ይህች ፡ መፈጠርን ፡ ወደማጥፋት ፡ በሚያደርስ ፡ ጥፋት ፡ የሥጋን ፡ ባሕርያት ፡ ስምምነት ፡ ታጠፋለችና። ዳግመኛም ፡ አካልን ፡ ወደማጕደል ፡ ታደርሳለች ።

፷፻፬ በተፈጥሮዋ ፡ የረከሰች ፡ ናት ፡ ብለው ፡ የከለከሏት ፡ አይደለም ። እግዚአብሔር ፡ ከፈጠረው ፡ ፍጥረት ፡ ወገን ፡ ናትና ። እግዚአብሔር ፡ የፈጠረው ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ መልካም ፡ እንደሆነ ፡

አንቀጽ ፡ ፳፫ ፡፡

ኵሎ ፡ ዘፈጠረ ፡ ከመ ፡ ሠናይ ፡ ውእቱ” ፡፡ ወበወንጌልኒ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ አኮ ፡ ኵሉ ፡ ዘይበውእ ፡ ውስተ ፡ አፈ ፡ ሰብእ ፡ ዘይክል ፡ አርኵሶቶ ፡፡ ወአፈ ፡ ወርቅኒ ፡ ይቤ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብጠለ ፡ በዝ ንቱ ፡ ቃል ፡ መብዝኅታ ፡ ለትእዛዘ ፡ ኦሪት ፡፡

፳፻፭ ወያጸንዕ ፡ ዘንተ ፡ ምክረ ፡ ዘተነግረ ፡ በአብረክሲስ ፡ ወውእቱ ፡ ቃለ ፡ ሉቃስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ዘይቤ ፡ ወዐርገ ፡ ጴጥሮስ ፡ መልዕልተ ፡ ናሕስ ፡ ጊዜ ፡ ፮ቱ ፡ ሰዓት ፡ ከመ ፡ ይጸሊ ፡ ወነዋ ፡ ርኅበ፡ ወይፈቅድ ፡ ይብላዕ ፡ ወእንዘ ፡ ያስተዳልዉ ፡ ሎቱ ፡ መጽአ ፡ ድቃስ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወርእየ ፡ ሰማየ ፡ ርኅወ ፡ ወናሁ ፡ ሞጣሕት ፡ ዘእኁዝ ፡ በ፬ቱ ፡ ጽንፈሁ ፡ እምሳለ ፡ ልብስ ፡ ዐቢይ ፡ እንዘ ፡ ይወርድ ፡ ዲበ ፡ ምድር ፡፡ ወሀሎ ፡ ውስቴቱ ፡ ኵሉ ፡ እንስሳ ፡ ዘ፬ቱ ፡ እገሪሁ ፡ ወኵሉ ፡ ዘይትሐወስ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ወአዕዋፈ ፡ ሰማይ ፡ ወመጽአ ፡ ቃል ፡ ኀቤሁ ፡ ዘይብል ፡ ተንሥእ ፡ እ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሕርድ ፡ ወብላዕ ፡፡ ወይቤሎ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሐሰ ፡ ሊተ ፡ እግዚእየ ፡ እስመ ፡ ኢበላዕኩ ፡ አነ ፡ ግሙራ ፡ ርኩሰ ፡ ወኢደነሰ ፡፡ ወዳግመ ፡ ጸውዖ ፡ ወይቤሎ ፡ “ዘእግዚአብሔር፡ አንጽሖ ፡ ኢታስተራኵስ ፡ አንተ ፡ ወኮነ ፡ ዝንቱ፡ ቃል ፡ ፫ተ ፡ ጊዜያተ” ፡፡

፳፻፮ ወቅዱሳንሂ ፡ መምህራን ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ወካልእኒሁ ፡ አበው ፡ ለበዉ ፡ አምዝንቱ ፡ ከመ ፡ መፍቅድ ፡ ኮነ ፡ በቱ ፡ ፪ቱ ፡ ምግባራት ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘኅቡእ ፡ ወውእቱ ፡ ከመ ፡ ኢነሐሊ ፡ እምይእዜ ፡ ከመ ፡ አሕዛብ ፡ እለ ፡ ኢአምኑ ፡ ዓዲሆሙ ፡ ርኩሳን ፡ እሙንቱ ፡ ዘኢይደልዎሙ ፡ ለምእመናን ፡ ተራክቦ ፡ ምስሌሆሙ ፡ በከመ ፡ አዘዘ ፡ ፍትሐ ፡ ብሊት ፡፡ ወካልእኒ ፡ ክሡት ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ነሐሊ ፡ ከመ ፡ ኵሎሙ፡ እንስሳት ፡ ንጹሓን ፡ እሙንቱ ፡ ወኢንትከላእ ፡ እምተሴስዮ ፡ ዘይደሉ ፡ እምልባዌ ፡ ጠባይዕ ፡ ወሲሳይኒ ፡ በሙ ፡ ሀሎ ፡ ዘእንበለ ፡ በሊዐ ፡ ደም ፡ ወሕኑቅ ፡ ወመሥዋዕተ ፡ ጣዖት ፡ ወብላዐ ፡ እርዌ ፡፡

፳፻፯ ወብዉሕ ፡ ለነ ፡ ከመ ፡ ኢንትከላእ ፡ እምነ ፡

ስለ ፡ መብልና ፡ ልብስ ፡ ስስቢትም ፡፡

አየ ፡ የሚል ፡ እነሆ ፡ በኦሪት ፡ ተጽፏልና ፡፡ (ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፳፩) ፡፡ በወንጌልም ፡ ወደሰው ፡ አፍ ፡ የሚገባ ፡ ሁሉ ፡ ሊያረክሰው ፡ የሚችል ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ ጌታችን ፡ ተናግሮአል ፡፡ (ማቴ ፡ ፲ ፡ ፲፩) ፡፡ አፈ ፡ ወርቅም ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ ቃል ፡ ከኦሪት ፡ ትእዛዝ ፡ ብዙውን ፡ አሳለፈ ፡ ብሏል ፡፡

፳፻፭ ይህንንም ፡ ቃል ፡ በግብረ ፡ ሐዋርያት ፡ የተነገረው ፡ ያጸናዋል ፡፡ ይኸውም ፡ ወንጌላዊ ፡ ሉቃስ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ ነው ፡፡ ስድስት ፡ ሰዓት ፡ ሊሆን ፡ ጴጥሮስ ፡ ሊጸልይ ፡ ከሰገነት ፡ ላይ ፡ ወጣ ፡፡ ያንጊዜ ፡ ተርቦ ፡ ሊበላ ፡ ሽቶ ፡ ነበር ፡፡ ምግቡንም ፡ እስኪያዘጋጁለት ፡ ድረስ ፡ እንቅልፍ ፡ መጣበት ፡፡ ሰማይ ፡ ተከፍቶ ፡ አየ ፡፡ በታላቅ ፡ ልብስ ፡ አምሳል ፡ በአራቱ ፡ ማዕዘን ፡ የተያዘ ፡ መጋረጃ ፡ ወደምድር ፡ ሲወርድ ፡ አየ ፡፡ በውስጡ ፡ አራት ፡ እግር ፡ ያለው ፡ እንስሳ ፡ በምድር ፡ የሚንቀሳቀስም ፡ ሁሉ ፡ የሰማይ ፡ ወፎችም ፡ አሉ ፡፡ ጴጥሮስ ፡ ሆይ ፡ ተነሥ ፡ አረድና ፡ ብላ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ወደርሱ ፡ መጣ ፡፡ ጴጥሮስም ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ እኔ ፡ ንጹሕ ፡ ያልሆነ ፡ የረከሰ ፡ ምግብ ፡ ከቶ ፡ በልቼ ፡ አላውቅምና ፡ ልበላ ፡ አይገባኝም ፡ አለው ፡፡ ዳግመኛም፡ ጠርቶ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያነጻውን ፡ አንተ ፡ አታርክሰው ፡ አለው ፡፡ ይህም ፡ ቃል ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ሆነ ፡፡ (የሐዋ ፡ ፲ ፡ ፱ - ፲፪) ፡፡

፳፻፮ ቅዱሳን ፡ መምህራን ፡ አፈ ፡ ወርቅና ፡ ሌሎችም አባቶች ፡ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ የሚያስፈልጉ ፡ ሁለት ፡ ነገሮች ፡ እንዳሉበት ፡ ተረዱ ፡፡ ከእነርሱም ፡ አንዱ ፡ ስውር ፡ ነው ፡፡ ይኸውም ፡ ገና ፡ ያላመኑ ፡ አሕዛብ ፡ በኦሪት ፡ ሕግ ፡ እንደታዘዘው ፡ ምእመናን ፡ ሊገናኙዋቸው ፡ የማይገባቸው ፡ ርኩሳን ፡ እንደሆኑ ፡ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ እንዳናስብ ፡ ነው ፡፡ (ዘሌዋ ፡ ፲፩ ፡ ፩ - ፵ ፡፡ ፳፪ ፡ ፳፫- ፺) ፡፡ ሁለተኛው ፡ ግን ፡ ግልጽ ፡ ነው ፡፡ ይኸውም ፡ አእምሮ ፡ ጠባይዕ ፡ ያለን ፡ ከመሆናችን ፡ የተነሣ ፡ እንስሳት ፡ ሁሉ ፡ ንጹሓን ፡ እንደሆኑ ፡ በውቀን ፡ የሚገባውን ፡ ከመመገብ ፡ እንዳንከለከል ፡ ነው ፡፡ ደምን ፡ ታንቆ ፡ የሞተውን ፡ ለጣዖት ፡ የተሠዋውን ፡ ከአውሬ ፡ የተረፈውን ፡ ከመብላት ፡ በቀር ፡ ምግብነት ፡ እነርሱ ፡ አሳቸው ፡፡

፳፻፯ አእምሮን ፡ ወደማጥፋት ፡ ባሕርይን ፡ ወደማናወጽ ፡ አካልን ፡ ወደማጕደል ፡ የሚያደርስ

### አንቀጽ ፡ ፳፫ ።

ዙሉ ፡ ግብር ፡ ዘእንበለ ፡ ዘአሕረሞ ፡ ፍትሐ ፡ ሕግ ፡ በእንተ ፡ ከዊኖቱ ፡ ዘያበጽሕ ፡ ኀበ ፡ ሙስና ፡ ሕሊና ፡ ወአማስኖ ፡ ጠባይዕ ፡ ወሙ ስና ፡ ሥጋ ። ወዝንቱ ፡ ይትከፈል ፡ ኀበ ፡ ፪ቱ ፡ ክፍል ። ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ በእንተ ፡ ዘኢይሜኒ፡ ለሲሳይ ፡ ወኢለመድኀኒት ፡ አኮ ፡ እምነ ፡ እን ስሳ ፡ ባሕቲቶ ፡ አላ ፡ እምነ ፡ በቍላትኒ ፡ካዕበ። ወዝንቱ ፡ ዘከመ ፡ እንስሳት ፡ እለ ፡ ቦሙ ፡ ሕምዝ ፡ ወዘከመ ፡ አራዊት ፡ መሣጥያን ፡ እለ ፡ ቦሙ ፡ ዕፍራት ፡ ወመጕረጽ ። ወእለ ፡ ይሴስዩ ፡ ሕምዛተ ፡ ወበቍላተኒ ፡ ቀተልያን ፡ እለ ፡ ያማስንዎ ፡ ለልብ ፡ ወለዙሉ ፡ ሥጋ ፡ በበሲፆቱ። ወላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ ፍትሕ ፡ እመ ፡ ተረክበ ፡ እምነ ዝንቱ ፡ ክፍል ፡ ፩ዱ ፡ ፆታ ፡ ዘያማስን ፡ ጥዑየ ፡ ወይፌውስ ፡ ድዉየ ፡ ይትገኀሥ ፡ ጥዑይ ፡ አም በሊፆቱ ፡ ወለድዉይሰ ፡ ብዉሕ ፡ ከመ ፡ ይብ ላዕ ፡ እመንገለ ፡ ፆታ ፡ መድኀኒት ። ወዳግማዊኒ ክፍል ፡ ዘይናፍቅ ፡ በመብልዕ ፡ አው ፡ ዘያናፍቅ ቢጸ ፡ ለእመ ፡ በልዐ ፡ ኪያሁ ።

### ስለ ፡ መብልና ፡ ልብስ ፡ ስለቤትም ።

ስለሆነ ፡ የሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ ከከለከለው ፡ በቀር፡ ከምግብ ፡ ሁሉ ፡ እንዳንከለክል ፡ መሆን ፡ ይገ ባናል ። (ዘሌዋ ፡ ፲፩ ፡ ፩ - ፵፯) ። ይህም ፡ ከሁ ለት ፡ ይከፈላል ። ከእነርሱም ፡ አንዱ ፡ ለምግብ ነትና ፡ ለመድኀኒት ፡ ስለማይጠቅም ፡ ነው ። መከልከላችንም ፡ ከእንስሳት ፡ ብቻ ፡ አይደለም እንዲሁም ፡ ከአትክልትም ፡ ነው ፡ እንጂ ። ይኸ ውም ፡ መርዝ ፡ ያላቸውን ፡ እንስሳት ፡ የሚነጣ ጥቁ ፡ አራዊትን ፡ ጥፍርና ፡ መውጊያ ፡ ያላቸ ውንና ፡ መርዞችን ፡ የሚመገቡ ፡ አራዊትን ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ከመብላት ፡ ከአትክ ልትም ፡ ወገን ፡ ቢበሏቸው ፡ አእምሮ ፡ የሚያ ጠፉትን ፡ አካል ፡ የሚያጎድሉትን ፡ ከመብላት ፡ እንድንከለክል ፡ ነው ። በዚህ ፡ እንቀጽ ፡ (ፍርድ) አትብሉ ፡ ከተባለው ፡ ወገን ፡ አንዱ ፡ ምግብ ፡ ጤነኛ ፡ ቢበላው ፡ የሚጎዳ ፡ በሽተኛ ፡ ቢበላው ፡ የሚፈውስ ፡ ቢሆን ፡ ጤነኛው ፡ እርሱን ፡ ከመ ብላት ፡ ይከልከል ። በሽተኛው ፡ ግን ፡ የሚያድ ነው ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ሊበላ ፡ ይገባዋል ። ሁለተኛውም ፡ ክፍል ፡ እየተጠራጠረ ፡ የሚበ ላውን ፡ ወይም ፡ እርሱ ፡ በልቶ ፡ ሌላውን ፡ እን ዲጠራጠር ፡ የሚያደርገውን ፡ ሰው ፡ ነገር ፡ ይና ገራል ።

፳፻፳ ወለአሉ ፡ ፪ቱ ፡ አክፋል ፡ አመረ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ በብሂሎቱ ፡ ውስተ ፡ መልእክተ ፡ ሮሜ ፡ ዘ፲ወ፰ቱ ። ወለዘኮነ ፡ ድኩመ ፡ ሃይማ ኖት ፡ አጽንዕዎ ፡ ወኢትኩኑ ፡ ኑፋቃነ ፡ በልብክሙ ፡ ወዙሉ ፡ ዘይትአመን ፡ ከመ ፡ ዙሉ ፡ ግብር ፡ ብዉሕ ፡ ለበሊዕ ፡ ይብላዕ ፡ ዙሎ ። ወድኩምሰ ፡ በፈቃዳቲሁ ፡ ይሴስይ ፡ ሐምለ ፡ ወኢያመንኖ ፡ ዘይበልዕ ፡ ዙሎ ፡ ለዘኢ ይበልዕ ። ወኢያኰንኖ ፡ ዘኢይበልዕ ፡ ለዘይበ ልዕ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀቤሁ ። ወናሁ ፡ ተዐውቀ ፡ ወአነ ፡ አትአመን ፡ በእግዚእነ ፡ ኢየ ሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከመ ፡ አልቦ ፡ ርኩስ ፡ በኀቤሁ ምንትኒ ። ወባሕቱ ፡ እመቦ ፡ ብእሲ ፡ ዘይትሔ ዘብ ፡ ከመ ፡ ርኩስ ፡ ውእቱ ፡ ሎቱ ፡ ለባሕቲቱ ፡ ይከውን ፡ ርኩስ ፡ እስመ ፡ ዙሉ ፡ ግብር ፡ ንጹሕ ፡ ውእቱ ፡ ወባሕቱ ፡ እኩይ ፡ ለብእሲ ፡ ሶበ ፡ በልዐ ፡ በዕቅፍት ። አመሰ ፡ ኢሠናይ ፡ ውእቱ ፡ ኢንብላዕ ፡ ሥጋ ፡ ወኢንስተይ ፡ ወይነ ፡ ወኢናምጽእ ፡ ግብረ ፡ ካልአ ፡ ዘይትዓ

፳፻፳ ለእነዚህ ፡ ለሁለቱ ፡ ክፍሎችም ፡ ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ በሮም ፡ መልእክቱ ፡ በ፲፬ኛው ፡ ምዕ ራፍ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አመለከተ ። ሃይማኖቱ ፡ ደካማ ፡ የሆነውን ፡ ሰው ፡ ቻሉት ። አጽናኑትም፡ በልባችሁም ፡ ተጠራጣሪዎች ፡ አትሁኑ ። ሁሉን ፡ ሊበሉት ፡ እንደሚገባ ፡ የሚያምን ፡ ሰው ፡ ሁሉን ፡ ይብላ ። የሚጠራጠር ፡ ግን ፡ እንደፈቃዱ ፡ ቅጠል ፡ ይብላ ። ሁሉን ፡ የሚበ ላው ፡ የማይበላውን ፡ አይንቀፈው ። የማይበላ ውም ፡ በሚበላው ፡ አይፍረድበት ። እግዚአብ ሔር ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ እንዳለ ፡ እነሆ ፡ ታውቋ ልና ። እኔ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ምንም ፡ ርኩስ ፡ ምግብ ፡ እንደሌለ ፡ አምናለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ርኩስ ፡ እንደሆነ ፡ የሚጠራጠር ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ንጹሕ ፡ ነውና ፡ ለእርሱ ፡ ብቻ ፡ ርኩስ ፡ ይሆንበታል ። ለሰው ፡ ክፉ ፡ የሚሆንበት ፡ ግን ፡ እየተጠራጠረ ፡ መብ ላቱ ፡ ነው ። እየተጠራጠሩ ፡ መብላት ፡ የሚ ጐዳ ፡ ከሆነስ ፡ ሥጋ ፡ እንብላ ፡ ወይንም ፡ አን

ቀፉ ፡ ቦቱ ፡ አኃዊነ ። ወዘሰ ፡ ናፈቀ ፡ ለአመ ፡ በልዐ ፡ ይትኴነን ፡ እስመ ፡ ኢገብረ ፡ ዘንተ ፡ በሃይማኖት ። ወኵሉ ፡ ዘኢኮነ ፡ በሃይማኖት ፡ ኃጢአት ፡ ውእቱ ።

፳፻፱ ወንሕነ ፡ አ ፡ ጉባኤ ፡ ጽኑዓን ፡ ይደልወነ ፡ ከመ ፡ ንፁር ፡ ድካመ ፡ ድኩማን ። ወበብሂሎቱ ፡ ካዕበ ፡ ውስተ ፡ መልእክቱ ፡ ቀዳማዊ ፡ ለሰብእ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ዘ፯ቱ ፡ ኵሉ ፡ ግብር ፡ ብውሑ ፡ ሊተ ፡ ወባሕቱ ፡ ኢመፍትው ፡ ከመ ፡ እረሲ ፡ ለመኑሂ ፡ ሥልጣነ ፡ በላዕሌየ ፡ እስመ ፡ መብልዕ ፡ ንቡር ፡ ለከርሥ ፡ ወከርሥኒ ፡ ንቡር ፡ ለመብልዕ ። ዘ፱ቱ ፡ ወበእንተ ፡ በሊዐ ፡ ዘይዘብሑ ፡ ለአማልክት ፡ ንሕነ ፡ ነአምር ፡ ከመ ፡ ጣዖት ፡ ኢኮነ ፡ ምንተኒ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ። ወከመ ፡ አልቦ ፡ እምላክ ፡ ዘእንበለ ፡ ፩ዱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባሕቲቱ ፡ ወባሕቱ ፡ አእምሮተ ፡ ግብርሰ ፡ ኢሀለወት ፡ በኀበ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ወመብልዕኒ ፡ ኢያቀርበነ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ አኮ ፡ በእንተ ፡ ዘበላዕነ ፡ ንሕነ ፡ ዘንትዌሰክ ፡ ወኢበእንተ ፡ ዘኢበላዕነ ፡ አኮ ፡ ዘነሐጽጽ ። ዑቁ ፡ ነጽሩ ፡ ይእዜ ፡ ከመ ፡ ሥልጣንክሙ ፡ ዕቅፍተ ፡ ለድኩማን ። ወከማሁ ፡ አመሰ ፡ ኮነ ፡ መብልዕ ፡ ያስሕት ፡ እኁየ ፡ ኢይበልዕ ፡ ሥጋ ፡ ለዝሉፉ ፡ ከመ ፡ ኢያስሕት ፡ እኁየ ። ዘ፳ወ፪ቱ ፡ ወናሁ ፡ ይደሉ ፡ ሊተ ፡ ኵሉ ፡ ግብር ፡ ወባሕቱ ፡ አኮ ፡ ኵሉ ፡ ዘይበቍዓኒ ፡ ወኵሉ ፡ ምግባር ፡ ብውሕ ፡ ሊተ ፡ ወባሕቱ ፡ አኮ ፡ ኵሉ ፡ ግብር ፡ ዘያሤኒ ፡ ወየሐንጽ ። ወኵሎ ፡ ዘይሠይጡ ፡ በምሥያጥ ፡ ብልዑ ፡ ወኢትሕትቱ ፡ በእንተ ፡ ሕሊናሁ ፡ ለዝንቱ ፡ እስመ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምድር ፡ በምልኣ ። ወአመቦ ፡ ዘጸውሀክሙ ፡ ፩ዱሂ ፡ እምአለ ፡ ኢየአምኑ ፡ ወፈቀድክሙ ፡ ከመ ፡ ትሑሩ፡ ብልዑ ፡ እምኵሉ ፡ ዘአቅረቡ ፡ ለክሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ትሕትቱ ። ወአመሰ ፡ ይቤለክሙ ፡ ዝንቱ ፡ ዘቡሕ ፡ ለአማልክት ፡ ኢትብልዑ ፡ በእንተ ፡ ቃለ ፡ ዝኩ ፡ ዘይቤለክሙ ። ወብሂሎቱኒ ፡ ለጢሞቴዎስ ፡ ዘ፬ቱ ፡ ወይትናገሩ ፡ በሕሡም ፡ ወየሐርሙ ፡ መባልዕተ ፡ ዘፈጠረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለበቍዔት ፡ ወለአኰቴት ፡ ለአለ ፡ የአምኑ ፡ ወየአምሩ ፡ ጽድቀ ፡ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ዘፈጠረ ፡

ጠጣ ። ወንድሞቻችን ፡ የሚጠራጠሩበትንም ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ አናምጣ ። የሚጠራጠር ፡ ግን ፡ እየተጠራጠረ ፡ ቢበላ ፡ ይፈረድበታል ። ይህን ፡ እምኖ ፡ አላደረገውምና ። በሃይማኖት ፡ ያልተደረገ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአት ፡ ነው ። (ሮሜ ፡ ፲፬ ፡ ፩ - ፳፫) ።

፳፻፲ በሃይማኖት ፡ ጸንተን ፡ የምንኖር ፡ እኛም ፡ የተጠራጣሪዎችን ፡ ደካማነት ፡ ልንታገሥ ፡ ይገባናል ። ዳግመኛም ፡ ለቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ በላከው ፡ በመጀመሪያው ፡ መልእክቱ ፡ በ፯ኛው፡ ክፍል ፡ እንዲህ ፡ አለ ። እነሆ ፡ ሥራው ፡ ሁሉ ፡ ይገባኛል ። ነገር ፡ ግን ፡ ማንም ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ እንዲሰለጥንብኝ ፡ አላደርግም ። መብል ፡ ለሆድ ፡ ሆድም ፡ ለመብል ፡ ዝግጁ ፡ ነው ። (፩ኛ ፡ ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፲፪) ። በዘጠንኛውም ፡ ክፍል ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ለጣዖታት ፡ የተሠዋውንም ፡ ስለመብላት ፡ ጣዖት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ምንም ፡ እንዳይደለ ፡ እኛ ፡ እናውቃለን ። ከአንድ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ እንደሌለ ፡ እናውቃለን ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ማወቅ ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ የለችም ። መብል ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አያቀርበንም ። እኛ ፡ ስለበላን ፡ የሚጨመርልን ፡ ስላልበላንም፡ የሚጐድልብን ፡ የለምና ። ሥልጣናችሁ ፡ (ፍላጐታችሁ) ፡ ለተጠራጣሪዎች ፡ እንቅፋት ፡ እንዳይሆን ፡ ዕወቁ ፡ ተጠንቀቁ ። እንደዚሁም ፡ መብል ፡ ወንድሜን ፡ የሚያስት ፡ ከሆነ ፡ ወንድሜን ፡ እንዳላስት ፡ ሥጋ ፡ ለዘወትር ፡ እልበላም ። (፩ኛ ፡ ቆሮ ፡ ፰ ፡ ፩ - ፲፫) ። በ፳፪ኛውም፡ ክፍል ፡ እንዲህ ፡ አለ ። እነሆ ፡ ሥራው ፡ ሁሉ ፡ ይገባኛል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሁሉ ፡ የሚጠቅመኝ ፡ አይደለም ። ሥራው ፡ ሁሉ ፡ ለእኔ ፡ የተገባ ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሥራው ፡ ሁሉ ፡ የሚዘጅ ፡ የሚጠቅም ፡ አይደለም ። በገበያ ፡ የሚሸጡትን፡ ሁሉ ፡ ብሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ስለዚህ ፡ ሰው ፡ ተጠራጣሪነት ፡ አትመራመሩ ። ምድር ፡ በመላዋ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ናትና ። ካላመኑት ፡ ወገን ፡ የጠራችሁ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ልትሄዱም ፡ ብትወዱ ፡ ሳትመራመሩ ፡ ያቀረቡላችሁን ፡ ሁሉ ፡ ብሉ ። ይህ ፡ ለጣዖት ፡ የተሠዋ ፡ ነው፡ ቢላችሁ ፡ ግን ፡ ስለነገራችሁ ፡ አትብሉ ። (፩ኛ ፡ ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፳፫ - ፳፱) ። ለጢሞቴዎስም ፡ በጻፈው በ፬ኛው ፡ ክፍል ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ። ለሚያም

እግዚአብሔር ፡ ሠናይ ፡ ውእቱ ፡ ወአልቦ ፡ ውስቴቱ ፡ ምንትኒ ፡ ምኑን ፡ ስበ ፡ ተወክፍዎ ፡ በአኰቴት ፡ ወኵሉ ፡ ይትቄደስ ፡ በቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወበጸሎት ።



ኑና ፡ ጽድቅን ፡ ለሚያውቁ ፡ ለዎች ፡ ለጥቅምና ፡ ለምስጋና ፡ እግዚአብሔር ፡ የፈጠራቸውን ፡ ምግቦች ፡ እየተዉ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ ይናገራሉ ። እግዚአብሔር ፡ የፈጠረው ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ በምስጋና ፡ ከተመገቡት ፡ ርኵሰት ፡ የሌለበት ፡ ንጹሕ ፡ ነውና ። ሁሉም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃልና ፡ በጸሎት ፡ ይቀደሳል ። (፩ኛ ፡ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፫ - ፭) ።

፰፻፲ በስ ፡ ፃወፀ፦ ፡ ወኢያርኵስ ፡ ቀሲስ ፡ ወኤጲስቆጶስ ፡ ምንተኒ ፡ እምነ ፡ መባልዕት ፡ ኵሎሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ዳእሙ ፡ ዘየሐርምዎ ፡ ባሕቲቶሙ ፡ በእንተ ፡ እግዚአብሔር ። ወይደልዎሙ ፡ ለመሚሐውያን ፡ ወለካህናት ፡ እለ ፡ እምውስቴቶሙ ፡ ወፈድፋደሰ ፡ ለመነኰሳት ፡ ከመ ፡ ኢይጸመዱ ፡ ለዝንቱ ፡ ለብዙኅ ፡ ጸታ ፡ መባልዕት ፡ ዘዘዚአሁ ፡ ወኢትፍግዕት ፡ በጣዕሙ ፡ ወዔናሁ ፡ ወልምላሜሁ ፡ ወኅብሩ ፡ ዘያጌጊ ። አላ ፡ ይሴሰዩ ፡ ለበቍዔት ፡ በዘይቀውም ፡ ሥጋ ፡ ኅዳጠ ፡ መዋዕለ ፡ ወዘተረከበ ፡ ለብዙኃን ፡ በመካናቲሆሙ ፡ ወዘመናቲሆሙ ። ወእግዚእነሂ ፡ ይቤ ፡ ምንትኑ ፡ ተደልዎ ፡ ወአስተሐምሞ ፡ በግብር ፡ ብዙኅ ፡ በዝንቱ ፡ ዓለም ። ወዘይትፈቀድሰ ፡ ንቤሁ ፡ ኅዳጥ ፡ ውእቱ ፡ ወ፩ዱ ፡ ውእቱ ። ወሐዋርያሁኒ ፡ ተለዎ ፡ ወይቤ ፡ አከለነ ፡ እምከመ ፡ ረከብነ ፡ ሲሳየነ ፡ ወዓራዘነ ። ወእግዚእነሂ ፡ ካዕበ ፡ ይቤ ፡ ተዓቀቡ ፡ እምጽጋብ ፡ ወስካር ፡ ወወሀበ ፡ ብዕዓነ ፡ ለርኁባን ፡ ወለፅሙአን ፡ በእንተ ፡ ጽድቅ ፡ ወረሰየ ፡ እሴቶሙ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ።

፰፻፲ በስ ፡ ፃ፪ ፡ እነርሱ ፡ ብቻ ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ ብለው ፡ ከሚከለከሉት ፡ በቀር ፡ ቄስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ከመባልዕት ፡ ወገን ፡ ሁሉ ፡ ማንኛውንም ፡ መብል ፡ ርኩስ ፡ ነው ፡ አይበል ። ከእነርሱ ፡ ወገን ፡ ለሚሆኑ ፡ ለምእመናንና ፡ ለካህናቱ ፡ ይልቁንም ፡ ለመነኰሳት ፡ ዓይነቱ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ለሚሆን ፡ ብዙ ፡ ምግብ ፡ ተገዦች ፡ እንዳይሆኑ ፡ ይገባቸዋል ። በጣዕሙ ፡ በመዓዛዉ ፡ በአለባበሱ ፡ በሚያስት ፡ መልኩ ፡ እንዳይደሰቱ ፡ መሆን ፡ ይገባቸዋል ። ሥጋ ፡ ለጥቂት ፡ ወራት ፡ ይቆም ፡ ዘንድ ፡ ለሚበቃ ፡ ያህል ፡ ይመገቡ ፡ እንጂ ። ለብዙዎች ፡ ሰዎች ፡ በዘመናቸውና ፡ በቦታቸው ፡ የተገኘውን ፡ ይመገቡ ፡ እንጂ ። ጌታችንም ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ ለብዙ ሥራ ፡ መዘጋጀትና ፡ መጨነቅ ፡ ምንድን ፡ ነው ? ለእርሱስ ፡ የሚያሻው ፡ ጥቂት ፡ ነው ። ያውም ፡ አንድ ፡ ነው ፡ አለ ። (ማቴ ፡ ፲፯ ፡ ፳፮ ። ሉቃ ፡ ፲ ፡ ፴፩-፴፪) ። ሐዋርያውም ፡ ምግባችንና ፡ ልብሳችንን ፡ ካገኘን ፡ ይበቃናል ፡ በማለቱ ፡ መሰለው ። (፩ኛ ፡ ጢሞ ፡ ፮ ፡ ፰) ። ዳግመኛም ፡ ጌታችን ፡ ከስካርና ፡ ከጥጋብ ፡ ተጠበቁ ፡ አለ ። (ሉቃ ፡ ፯ ፡ ፳፭ ። ማቴ ፡ ፳ ፡ ፵፰ -፵) ። ስለጽድቅ ፡ ብለው ፡ ለሚራቡና ፡ ለሚጠሙ ፡ ብፅዕናን ፡ ሰጠ ። ዋጋቸውንም ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ አደረገ ። (ማቴ ፡ ፭ ፡ ፮ ። ሉቃ ፡ ፮ ፡ ፳፩) ።

፰፻፲፩ ወበእንተ ፡ አልባስኒ ፡ ናሁ ፡ ተነግረ ፡ በእንቲአሆሙ ፡ በበገጹ ፡ ዘይከውን ፡ እምኔሆሙ ፡ ወከልአ ፡ እምቀጠንት ፡ ዘያሠረግውዎሙ ፡ በኅብራት ፡ ዘገለፉ ፡ ቦሙ ፡ ወከመ ፡ ይኩን ፡ ለመልእክተ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ልብስ ፡ ፀዓዳ ፡ ድልው ። ወከመሂ ፡ ኢይልበሳ ፡ አንስት ፡ አልባስ ፡ እደው ፡ ወእደውኒ ፡ አልባስ ፡ አንስት ፡ ወኢያደዩ ፡ እደው ፡ ሕልቀታተ ፡ ውስተ ፡ አፃብዒሆሙ ፡ ወኢአንስት ፡ ከመ ፡ ኢይልበሳ ፡ ወርቀ ፡ ዘተገብረ ፡ በልብስ ፡ ዘያስተሜክሕ ።

፰፻፲፩ ስለልብሶችም ፡ በያይነቱ ፡ እነሆ ፡ ተነገረ ። በቀለም ፡ ያስጌጧቸውን ፡ ልብሶች ፡ ከመልበስ ፡ ከለከለ ። ለቤተ ፡ መቅደስ ፡ ማገልገያ ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ። ሴቶች ፡ የወንዶችን ፡ ልብስ ፡ ወንዶችም ፡ የሴቶችን ፡ ልብስ ፡ እንዳይለብሱ ፡ ወንዶች ፡ በጣቶቻቸው ፡ የምንዝር ፡ ጌጥ ፡ ቀለበት ፡ እንዳያደርጉ ፡ ሴቶችም ፡ ከወርቅ ፡ የተሠራ ፡ የሚያስመካ ፡ ወርቀ ፡ ዘቦ ፡ ግምጃ ፡ እንዳይለብሱ ፡ ከለከለ ።

አንቀጽ ፡ ፳፫ ።

፳፻፲፪ ወይልበሱ ፡ ዕሙዳን ፡ ልብሰ ፡ ገዚፈ ፡ እምነ ፡ ፀምር ፡ ወዘይመስሎ ፡ ለገንቱ ። ወበእንተ ፡ ኅሩያንሰ ፡ ኢፈለጠ ፡ እምነበ ፡ አይቴ ፡ መባሕት ፡ ሎሙ ፡ ወይደሉ ፡ ኵሉ ፡ ለለፈዱ ፡ ከመ ፡ ይልበሱ ፡ ወይሠርገዉ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝብ ፡ በፈቃዶሙ ፡ በጣዕመ ፡ ዘመን ፡ ወስብእ ፡ መገብቱ ።

፳፻፲፫ ወኢይልበሱ ፡ ካህናት ፡ ልብሰ ፡ ሐሪ ፡ ወልብሰ ፡ ሐናጺ ፡ ወልብሰ ፡ ጠቢባን ፡ ወእምነ ፡ ዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ ኢይደልዎሙ ፡ ለእርድእተ ፡ ክርስቶስ ፡ ከመ ፡ ይልበሱ ፡ ወይትዓቀቡ ፡ እምነ ፡ እሉ ፡ አልባሳት ። እስመ ፡ እግዚእነ ፡ መሀሮሙ ፡ ለአርዳኢሁ ፡ ከመ ፡ ኢያብዝኁ ፡ አልባሰ ፡ ወንእዶ ፡ ለዮሐንስ ፡ መጥምቅ ፡ በእንተ ፡ ዘኢለብሰ ፡ እምነ ፡ እሉ ፡ ኅብራት ፡ ዘውእቶሙ ፡ አልባሰ ፡ ተድላት ። ወዘይመስልዎ ፡ ትሩፋን ፡ ነቢያት ፡ ወሐዋርያት ፡ ቅዱሳን ፡ ወጠቢባን ፡ ዘኢለብሱ ።

፳፻፲፬ ወናሁ ፡ ይቤ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ለምእመናንሰ ፡ ይደልዎሙ ፡ ከመ ፡ ይትዓወቁ ፡ እምነ ፡ ማእዶሙ ፡ ወሥርጋዌሆሙ ፡ ወነገሮሙ ፡ ወማእዞሙ ፡ ወዘይመስልዎሙ ፡ ለእሉ ። እስመ ፡ ሕግነ ፡ ናሁ ፡ እቀመቱነ ፡ ወአርኀቀተነ ፡ እምነ ፡ ዝንቱ ፡ ኵሉ ። ወጠቢብኒ ፡ ቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ ይቤ ፡ ይደሉ ፡ ለነ ፡ ከመ ፡ ንሥራዕ ፡ ልብሰነ ፡ በዘንከድን ፡ ዕርቃነነ ፡ ወንትመጠው ፡ በዘይትፌጸም ፡ ፈቃድነ ፡ ወንድኅን ፡ እምቍር ፡ ወዋዕይ ፡ ወንዕቀብ ፡ ቀኖና ፡ ዕሙዳን ።

፳፻፲፭ ወዐቂበ ፡ ዝንቱ ፡ ቀኖና ፡ ይደሉ ፡ ለነ ፡ ከመ ፡ ንትፈለጥ ፡ እምሕዝባውያን ፡ ወለሕዝባውያንሰ ፡ ይኩን ፡ ዘይትረከብ ፡ ሎሙ ፡ ለመብዝኅቶሙ ፡ ወለመነኰሳትሰ ፡ ይኩን ፡ ልብሶሙ ፡ አልባሰ ፡ ፀምር ፡ ገዚፍ ።

፳፻፲፮ ወበእንተ ፡ ማኅደራትኒ ፡ ይደሉ ፡ በአምሳነ ፡ ዛቲ ፡ ሕግ ፡ ዘኮነት ፡ ለትሩፋን ፡ ወለመናንያን ፡ ኀላፍያተ ፡ ወዘየኀሥሡ ፡ ነባርያተ ፡

ስለ ፡ መብልና ፡ ልብስ ፡ ስለቤትም ።

፳፻፲፪ መናንያን ፡ ከጠጕር ፡ ወገን ፡ የተሠራ ፡ ደኃሳ ፡ ልብስና ፡ ይህንንም ፡ የሚመስለውን ፡ ይልበሱ ። ለሹማምት ፡ ግን ፡ ማንኛውንም ፡ አልለየም ። ሁሉን ፡ ሊለብሱ ፡ ይገባቸዋል ። ሁሉም ፡ ለእየንዳንዳቸው ፡ ሊለብሱ ፡ ይገባል ። ሕዝቡም ፡ የሹማምቱም ፡ ቤተሰቦች ፡ ዘመን ፡ ባስገኘውና ፡ በወደዱት ፡ ልብስ ፡ ያጊጡ ።

፳፻፲፫ ካህናት ፡ የወታደርና ፡ የእናጢ ፡ የጠቢቦችንም ፡ ልብስ ፡ አይልበሱ ። ክርስቶስን ፡ የሚያገለግሉ ፡ ካህናት ፡ ከዚህ ፡ ከተነገረው ፡ ሁሉ ፡ ሊለብሱ ፡ አይገባቸውም ። እንደ ፡ እነዚህ ፡ ያሉትንም ፡ ልብሶች ፡ ከመልበስ ፡ ይከልከሉ ። ጌታችን ፡ ለደቀመዛሙርቱ ፡ ልብስ ፡ እንታብዙ ፡ ብሎ ፡ አስተምሮአቸዋልና ። (ሉቃ ፡ ፫ ፡ ፲ - ፲፩) ። ቀለም ፡ የገቡትን ፡ እነዚህን ፡ ልብሶች ፡ ባለመልበሱ ፡ ዮሐንስ ፡ መጥምቅን ፡ አመስግኖታልና ። (ማቴ ፡ ፲፩ ፡ ፯ - ፲፩ ። ሉቃ ፡ ፯ ፡ ፳ - ፳፰) እነዚህም ፡ የተድላ ፡ ልብሶች ፡ ናቸው ። እንደ ፡ እርሱ ፡ ያልለበሱትንም ፡ ትሩፋን ፡ ነቢያትን ፡ ቅዱሳን ፡ ሐዋርያትን ፡ ጠቢባንንም ፡ አመስገናቸው ።

፳፻፲፬ እነሆ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅም ፡ እንዲህ ፡ አለ ። መነኮሳትስ ፡ ከማዕዳቸው ፡ መቅለል ፡ ከልብሳቸው ፡ መኰስቈል ፡ ከነገራቸው ፡ አለመሰብቀል ፡ ከጠባያቸው ፡ ማማር ፡ ይህንም ፡ የመሰለ ፡ ሥራ ፡ ከመሥራታቸው ፡ የተነሣ ፡ ሊታወቁ ፡ ይገባል ። እነሆ ፡ ሕጋችን ፡ ወሰናናለችና፡ ከመጥፎውም ፡ ሁሉ ፡ አርቃናለችና ። ብልሁ ፡ ቅዱስ ፡ ባስልዮስም ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ዕርቃናችንን ፡ የምንሸፍንበት ፡ ፈቃዳችን ፡ የሚፈጸምበትን ፡ ከሌሊት ፡ ቍር ፡ ከቀን ፡ ሐሩር ፡ የምንድንበትን ፡ ልብስ ፡ ወስነን ፡ ልንቀበል ፡ ይገባናል ። የመነኮሳትንም ፡ ሕግ ፡ ልንጠብቅ ፡ ይገባናል ።

፳፻፲፭ ከሕዝባውያን ፡ እንለይ ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ ሥርዓት ፡ መጠበቅ ፡ ለእኛ ፡ ይገባናል ። ለብዙዎቹ ፡ ሕዝባውያን ፡ ግን ፡ የተገኘው ፡ ይሁንላቸው ። ለመነኮሳት ፡ ግን ፡ ልብሳቸው ፡ ከጠጕር ፡ የተሠራ ፡ ደኃሳ ፡ ይሁን ።

፳፻፲፮ ስለ ፡ ቤቶችም ፡ አሠራር ፡ ነገር ፡ ኀላፊውን ፡ ዓለም ፡ ንቀው ፡ የማያልፈውን ፡ ለሚሹ ፡ መናንያን ፡ በዚች ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ሊሆን ፡ ይገ

ይኩን ፡ ሲሳዮሙ ፡ ወዓራዘሙ ፡ በከመ ፡ ተሠርዐ ፡ ሎሙ ፡ ዘውእቱ ፡ አስስሎተ ፡ ምንዳቤ ፡ ባሕቲቲ ። ወከማሁ ፡ ፍትሕ ፡ በእንተ ፡ ገቢረ ፡ ማኅደር ፡ በዘትበቍዕ ፡ ይእቲ ፡ ለእለ ፡ ይትጋብኡ ፡ ባቲ ፡ በዘተኀብእሙ ፡ ወያስተጋብኡ ፡ ሲሳዮሙ ፡ ዘተሠርዐት ፡ ሎሙ ።

፳፻፲፯ ወእግዚእነሂ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አዘዘ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ሀልዎትነ ፡ በተመስሎተ ፡ ምግባራቲሁ ፡ አመ ፡ ሥጋዌሁ ፡ እንተ ፡ መሀረነ ፡ ኪያሃ ፡ ንሑር ፡ በትሩፋት ፡ በቃሉ ፡ ወበምግባሩ ። ወይቤለነ ፡ ሎቱሰ ፡ አልቦቱ ፡ ማኅደር ፡ ወኢኀበ ፡ ዘያሰምክ ፡ ርእሶ ።

፳፻፲፰ ወሐዋርያሁኒ ፡ ዘተለዎ ፡ ወይሰሙ ፡ ለእለ ፡ የኀድሩ ፡ ውስተ ፡ ጸላዕት ፡ ወግበበ ፡ ምድር ፡ ወይቤ ፡ እስመ ፡ ኢይደልዎሙ ፡ ዓለም ። ወቅዱሳንኒ ፡ ወጠቢባን ፡ ኮኑ ፡ ይኄልቁ ፡ ርእሶሙ ፡ በዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ከመ ፡ ነጋድያን ፡ ወፈላስያን ፡ ወአማን ፡ ውእቱ ፡ ግብረ ፡ ሕይወትነ ፡ በዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ይከውን ፡ ከማሁ ።

፳፻፲፱ ወአፈ ፡ ወርቅኒ ፡ ይቤ ፡ በተግሣጹ ፡ እስመ ፡ ማኅደረ ፡ እንግዳ ፡ ወነጋድያን ፡ ዕውቅ ፡ ውእቱ ፡ በዘየኀሥሥዎ ፡ ወይትገበር ፡ ሎሙ ፡ በአምጣነ ፡ መፍቅዶሙ ፡ ዘበውእቱ ፡ ጊዜ ። ወዘሰ ፡ ይሬእያ ፡ ለይእቲ ፡ ማኅደር ፡ ድኅሬዊት ፡ መለኮታዊት ፡ ለማያዊት ። ወኀሠሣ ፡ ወኀለየ ፡ በልቡ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ኢይነብር ፡ ውስተ ፡ ዛቲ ፡ ማኅደር ፡ ምድራዊት ፡ እንበለ ፡ ኅዳጥ ፡ ዘመን ። ለምንትኬ ፡ ይፀዕር ፡ በእንተ ፡ ርኂበ ፡ ዛቲ ፡ ማኅደር ፡ ወጽንዓታ ፡ ወለምንት ፡ ይኄልሕ ፡ በእንተ ፡ ዘየኀልፍ ፡ እንዘ ፡ መስተሠንይ ።

፳፻፳ ወበእንተ ፡ ግብረ ፡ እድሰ ፡ ዘለንታሁ ፡ ብውሕ ፡ ውእቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ዳእሙ ፡ ዘይትቃረና ፡ ለፈቃደ ፡ ሕግ ፡ እምግባራት ፡ ዓለማውያት ፡ ዘከመ ፡ ሥራይ ፡ ወጠንቍሎ ፡ እው ፡ ግብር ፡ ከመ ፡ ገቢረ ፡ ጣዖት ፡ ወንዋያቲሁ ፡ ወጸዋዕያን ፡ ወጠንቋልያን ፡ ወዘፋንያን ፡ ወዘከመ ፡ ተውኔት ፡ ወእጽሕሶ ፡ በእግር ።

፳፻፳፩ ወከማሁ ፡ ይቤ ፡ አቡሊዲስ ፡ በቀኖናቲሁ ፡ ፲ወ



ባል ። ምግባቸውና ፡ ልብላቸውም ፡ እንደተወሰነላቸው ፡ ይሁን ። ይኸውም ፡ ችግርን ፡ ማቅለል ፡ ብቻ ፡ ነው ። ስለቤት ፡ አሠራር ፡ የሚወስነውም ፡ ሥርዓት ፡ ለሚኖሩባት ፡ ሰዎች ፡ የምትጠቅም ፡ መጠለያ ፡ ትሆንላቸው ፡ ዘንድ ፡ የተወሰነላቸውንም ፡ ምግብ ፡ ለማኖር ፡ የምትችል ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

፳፻፲፯ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ በሥጋዌው ፡ ጊዜ ፡ በትሩፋት ፡ እንድንኖር ፡ አነዋራችን ፡ በቃሉም ፡ በምግባሩም ፡ ያስተማረንን ፡ እርሱ ፡ ይሠራው ፡ የነበረውን ፡ አስመስሎ ፡ በመሥራት ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ። እርሱ ፡
ፉ ማደሪያ ፡ ወይም ፡ ራሱን ፡ የሚያስጠጋበት ፡ እንዳልነበረው ፡ ነገረን ። (ማቴ ፡ ፰ ፡ ፳) ።

፳፻፲፰ እርሱን ፡ የተከተለው ፡ ሐዋርያውም ፡ በዋሻና ፡ በፉርከታ ፡ የሚኖሩትን ፡ ሰዎች ፡ ዓለም ፡ የማይገባቸው ፡ እኒህ ፡ ናቸውና ፡ ብሎ ፡ አመሰገናቸው ። (ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፴፰) ። በዋቂዎች ፡ ቅዱሳንም ፡ ራሳቸውን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ እንደ ፡ መሸ ፡ አዳሪዎች ፡ እንደ ፡ ስደተኞች ፡ የሚቆጥሩ ፡ ሆኑ ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሕይወታችን ፡ ሥራ ፡ በእውነት ፡ እንደዚሁ ፡ ይሆናል ።

፳፻፲፱ አፈ ፡ ወርቅም ፡ በተግሣጹ ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ለእንግዶችና ፡ ለመንገደኞች ፡ የሚያሻቸው ፡ ማደሪያ ፡ የታወቀ ፡ በሰሆን ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በሚያሻቸው ፡ ልክ ፡ ይሆንላቸዋል ። በኋላ ፡ ዘመን ፡ መለኮት ፡ የሚያወርላትን ፡ ያችን ፡ ሰማያዊቱን ቤት ፡ በዓይኑ ፡ ልቡና ፡ ያያት ፡ ሰው ፡ በዚች ፡ በምድራዊቱ ፡ ቤት ፡ ከጥቂት ፡ ዘመን ፡ በቀር ፡ እንደማይኖርባት ፡ እያወቀ ፡ በሰዚች ፡ ምድራዊት ፡ ቤት ፡ ለሰፋትና ፡ ለጽናቷ ፡ ለምን ፡ ይጨነቃል ? ። አምሮ ፡ ሳለ ፡ በሰሚያልፈውስ ፡ ዓለም ፡ ለምን ፡ ያዝናል ? አለ ።

፳፻፳ ስለ ፡ ተግባረ ፡ እድ ፡ ግን ፡ በዓለም ፡ ከሚሠሩ ፡ ሥራዎች ፡ የሕግን ፡ ፈቃድ ፡ ከሚቃወማት ፡ ሥራ ፡ በቀር ፡ ሁሉን ፡ ሊሠራ ፡ ይገባል ። ይኸውም ፡ እንደ ፡ ሥራይ ፡ እንደ ፡ ጥንቈላ ፡ ወይም ጣዖትንና ፡ መገልገያዎቹን ፡ እንደመሥራት ፡ እንደ ፡ ጋኔን ፡ ሳቢዎችና ፡ እንደ ፡ ጠንቋዮች ፡ እንደ ፡ ዘፋኞች ፡ እንደ ፡ መጥፎ ፡ ጨዋታ ፡ በእግር ፡ እንደማሽብሸብ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ነው ።

፳፻፳፩ አቡሊድስም ፡ ከቀኖናዎቹ ፡ በ፲፩ኛው ፡ ክፍል ፡

አንቀጽ ፡ ፳፫ ።

፩፶. ፡ ወኵሉ ፡ ነሃቢ ፡ ብሩር ፡ ይትዐቀብ ፡ ከመ ፡
ኢይግበር ፡ ጣዖተ ፡ ወኢይኩን ፡ ነሃቢ ፡ ምስል ፡
ወኢሠዓሌ ፡ ወእለ ፡ ተርፉ ፡ ኪናተ ።
ወለእመ ፡ ቀረበ ፡ ፩፶ሂ ፡ እምድኅረ ፡ ጥም
ቀት ፡ እንዘ ፡ ይገብር ፡ ዘከመዝ ፡ ግብረ ፡ ዘኢ
ደሉ ፡ ለሰብእ ፡ ይትፈለጡ ፡ እስከ ፡ ይኔስሑ ።

፳፻፳፪ ሥርዋጽ ፡ ነገሩ ፡ ቀኖናት ፡ ዘተጽሕፉ ፡ ለመ
ሢሐውያን ፡ ዘ፲ወ፱ቱ ፡ ፳፡ እምትእዛዘ ፡ ጳው
ሎስ ፡ ኵሉ ፡ ዘይገብር ፡ ግብረ ፡ ጣዖት ፡ ወእለ ፡
ይነፍኑ ፡ እንዚራተ ፡ ወዘፋንያን ፡ ወመፍቀር
ያነ ፡ መዊዕ ፡ ወዘይመስሎሙ ፡ ይትገኀሡ ፡
ወእመ ፡ አኮ ፡ ይፃእ ። ወዕጢቅ ፡ ውእቱ ፡
ከመ ፡ ግብራት ፡ ዘአቅደምነ ፡ ዘክርናሆሙ ፡ ኢይ
ደሉ ፡ ገቢሮቶሙ ፡ ኢይፈቅድዎሙ ፡ ሰብእ ፡
በጥዩቅ ፡ ይኄይስ ፡ ይትኃጥኡ ፡ እሉ ፡ እምይት
ኀጣእ ፡ ሰብእ ።

፳፻፳፫ ወዘይደሉስ ፡ ለመሢሐውያን ፡ እምነ ፡ ግብ
ራት ፡ ለሕይወተ ፡ ሥጋ ፡ ፪ቱ ፡ ክፍል ፡ ፩፶ ፡
እምኔሆሙ ፡ ዘይትፈቀድ ፡ ለበቍዔተ ፡ ሥጋ ፡
ወገብንቱ ፡ ውእቱ ፡ ዘረእ ፡ ወዐጺድ ፡ ለአስተጋ
ብኦ ፡ ሲሳይ ፡ ወእሥግሮት ፡ ወእኒም ፡ ወሰ
ፍየ ፡ አልባስ ፡ ወንድቀት ፡ ወመጋብርት ፡ ለማ
ኅደር ፡ ወገቢረ ፡ ፈውስ ፡ ለረኪበ ፡ ጥዒና ፡ ወእ
ሰስሎ ፡ ደዌያት ።

፳፻፳፬ ወክፍል ፡ ካልእ ፡ በዘኢትትፈጸም ፡ ሎሙ ፡
ገቢረ ፡ እሉ ፡ ግብራት ፡ ወአሥልጦታ ፡ ወኵሉ፡
ዘይገብሩ ፡ ዘእንበለ ፡ በእሉ ፡ ዘውእቶሙ ፡
ፀራቢ ፡ ወነሃቢ ፡ ወጸሓፊ ፡ ወዘየሐርዕ ፡ ወበ
ዓለ ፡ እቶን ፡ ውነባዚ ፡ ወበዓለ ፡ ኀብር ፡ ወመ
ምህር ፡ ወነጋዲ ። እስመ ፡ ነጊድስ ፡ ይትፈቀድ፡
በግብር ፡ ለአፍልሶ ፡ ዘሀሎ ፡ ውስተ ፡ አሐቲ
ሀገር ፡ ኀበ ፡ ካልእታ ። ወይትለእከዋ ፡ ላቲ ፡
ኖትያት ፡ ወመስተገብራን ። ወይደሉ ፡ ከመ ፡
ይትመሀሩ ፡ እምኵሉ ፡ ግብር ፡ ዘእሉ ፡ ግብ
ራት ፡ ለእቅሞተ ፡ መፍቅደ ፡ ዕፀብ ፡ ባሐቲቱ ።

፳፻፳፭ ወኢትሚጥ ፡ ኵሎ ፡ ጸሕቀከ ፡ በእንተ ፡ እግዚ
እት ፡ ወበእንተ ፡ እብዝኖ ፡ ተክለ ፡ ፍሬያት ፡

ስለ ፡ መብልና ፡ ልብስ ፡ ስለቤትም ።

እንዲህ ፡ አለ ። አንጥረኛ ፡ ሁሉ ፡ ጣዖት ፡ እንዳ
ይሠራ ፡ ይከልከል ። የጣዖቱን ፡ ምስል ፡ የሚ
ሠራና ፡ የሚሥል ፡ የቀሩትንም ፡ ለጣዖት ፡ የሚ
ያስፈልጉትን ፡ ጥበባት ፡ የሚሠራ ፡ እይሁን ።
አንድ ፡ ሰው ፡ እንኳ ፡ ከተጠመቀ ፡ በኋላ ፡
ምእመናን ፡ ሊሠሩት ፡ የማይገባውን ፡ እንደ
ዚህ ፡ ያለውን ፡ ሥራ ፡ ሲሠራ ፡ ቢገኝ ፡ በንስሐ ፡
እስኪመለስ ፡ ድረስ ፡ ከምእመናን ፡ ይለይ ።

፳፻፳፪ ሥርዋጽ ፡ ለክርስቲያን ፡ የተጻፉ ፡ መጻሕፍት ፡
እንዲህ ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ። ከጳውሎስ ፡ ትእ
ዛዝ ፡ ፲፱ኛውና ፡ ፳ኛው ፡ ክፍል ፡ ጣዖትን ፡
የሚሠራ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ለጣዖት ፡ እንዚራ ፡
የሚመቱና ፡ የሚዘፍኑ ፡ ለጣዖቱም ፡ በሚያደ
ርጉት ፡ ውድድር ፡ አሸናፊነትን ፡ የሚወዱና ፡
ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ
ከዚህ ፡ ሥራ ፡ ይከልከሉ ። አለዚያም ፡ ከምእ
መናን ፡ ይለዩ ። እንደዚህ ፡ ያሉት ፡ ሥራዎች ፡
ሊሠሩ ፡ አይገባም ፡ ብለን ፡ አስቀድመን ፡ እን
ደተናገርነው ፡ ሰዎች ፡ በእርግጥ ፡ የማይፈቅዱዋ
ቸው ፡ መሆናቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ሊላው ፡
ሰው ፡ ከሚታጣ ፡ እሊህ ፡ ቢታጡ ፡ ይሻላል ።

፳፻፳፫ ለሥጋ ፡ ሕይወት ፡ ያህል ፡ ከሥራዎች ፡ ውስጥ ፡
ለክርስቲያን ፡ የሚገቡት ፡ ሁለት ፡ ክፍሎች ፡
ናቸው ። ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ ለሥጋ ፡ ጥቅም ፡
ሊሆን ፡ የሚፈለግ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ምግብን ፡
ለማዘጋጀት ፡ መዝራትና ፡ ማጨድ ፡ ወጥመድ ፡
ማጥመድና ፡ ልብስ ፡ መሥራት ፡ መስፋት ፡
ቤት ፡ መሥራት ፡ ለቤት ፡ ሥራ ፡ የሚያስፈል
ጉትን ፡ መሣሪያዎች ፡ ማዘጋጀት ፡ ጤናን ፡ ለማ
ግኘትና ፡ ደዌን ፡ ለማራቅ ፡ መድኃኒት ፡ ማዘጋ
ጀት ፡ ነው ።

፳፻፳፬ ሁለተኛውም ፡ ክፍል ፡ በእነዚህ ፡ ካልሆን ፡ በቀ
ር ፡ እሊህን ፡ ሥራዎች ፡ ለማዘጋጀት ፡ የሚሠ
ራው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ የማይፈጸም ፡ መሆኑን ፡
ይናገራል ። እነዚሁም ፡ አናጢ ፡ አንጥረኛ ፡
ጸሐፊ ፡ ሬሙታ ፡ (ሬሜዩ) ፡ እሳት ፡ አንዳጅ ፡
ጋጋሪ ፡ ቀለም ፡ አግቢ ፡ አስተማሪ ፡ ነጋዴ ፡
ናቸው ። ንግዱም ፡ እኮ ፡ ከአንድ ፡ ሀገር ፡ የሚ
ገኘውን ፡ ወደማይገኝበት ፡ ሌላ ፡ ሀገር ፡ ለማድ
ረስ ፡ በግድ ፡ ያሻል ። መርከበኞችና ፡ ቀዘፊዎች፡
ይገለገሉበታል ።

፳፻፳፭ ግዳጅን ፡ ለመፈጸም ፡ ብቻ ፡ ከእሊህ ፡ ከተዘረዘ
ሩት ፡ ሥራዎች ፡ ውስጥ ፡ ይማሩ ፡ ዘንድ ፡ ይገ

ወአብዝኆ ፡ ጽጌያት ፡ ወኢበእንተ ፡ እንመት ፡ ላዕለ ፡ ኅብረተ ፡ ልብስ ፡ ወአብዝኆ ፡ እንመታት ፡ ወኢበእንተ ፡ ሕንጸ ፡ ወአሠርግዎ ፡ ማኅደር ፡ ወአፈድፍዶ ፡ ስፋሐታ ፡ ወተልዐሎታ ። ወናሁ ፡ እመረ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ነገር ፡ ትርጓሜ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ጠቢብ ፡ ጊዜ ተርጐሞ ፡ ስብሥረተ ፡ ማቴዎስ ።



ባል ። ስለሆነም ፡ አሳብዘን ፡ ሁሉ ፡ ብዙ ፡ ወደ መዝራት ፡ የፍሬ ፡ ተክሎችንና ፡ የአበባ ፡ ዛፎችን ፡ አብዝቶ ፡ ወደመትከል ፡ ብዙ ፡ ቀለም ፡ ያላቸውን ፡ ልብሶች ፡ ወደመሥራትና ፡ ሌላውንም ፡ ልብስ ፡ አብዝቶ ፡ ወደመሥራት ፡ ብዙ ፡ ቤት ፡ ወደመሥራት ፡ ቤትን ፡ ወደማስጌጥ ፡ ወርዱንና ፡ ቍመቱን ፡ ወደማሳደግ ፡ ብቻ ፡ አትመለስ ። እነሆ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈወርቅ ፡ የማቴዎስን ፡ ወንጌል ፡ በተረጐመበት ፡ አንቀጽ ፡ የዚህን ፡ ነገር ፡ አስረዳ ።

## አንቀጽ ፡ ፳ወ፭ቱ ።

በእንተ ፡ ፍኅረት ፡ ወሕዜ ፡ ወአውስቦ ፡ ወዘይተልዎ ፡ ለዝንቱ ።

፰፻፸፯ ወውእቱ ፡ ፯ቱ ፡ ምዕራፋት ። ምዕራፍ ፡ ቀዳማዊ ፡ እምቅድመ ፡ ንንግር ፡ በእንተ ፡ ተዋስቦ ፡ ይደልወነ ፡ ከመ ፡ ንዝክር ፡ ነገረ ፡ ቀዳማዌ ፡ እስመ ፡ ለመፍቅድ ፡ ቀዳማዊ ፡ ቦቱ ፡ ፪ቱ ፡ ግብራት ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ወሊደ ፡ ውሉድ ፡ ለአትርፎ ፡ ዘርእ ። ወይመርሕ ፡ ኀበ ፡ ዝንቱ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘይቤሎሙ ፡ ለእምኔው ፡ ወለእምኔውት ፡ ቀዳማውያን ፡ ብዝኁ ፡ ወተባዝኁ ፡ ወኢይከውን ፡ ዝንቱ ፡ ዘእንበለ ፡ በተራክቦ ፡ ለወሊድ ።

፰፻፸፰ ወዓዲ ፡ ሶበ ፡ ተተክለት ፡ ፍትወት ፡ በጠባይዕ ፡ እንስሳዊት ፡ ከመ ፡ ይትፈጸም ፡ ኀሠሣ ፡ ተራክቦ ፡ ዘይከውን ፡ እምኔሁ ፡ ዘርእ ። ወዝንቱ ፡ ላዕለ ፡ ፪ቱ ፡ መፍቅዳት ፡ መጥዎ ፡ ፍትወት ፡ በተራክቦ ፡ ለወሊድ ፡ ወዳግማዊኒ ፡ ረድኤት ፡ ዘትከውን ፡ ማእከለ ፡ ውሉባን ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ለካልኡ ፡ በእንተ ፡ እቅልሎ ፡ ድካም ፡ በዝንቱ ፡ ሕይወት ። ወይመርሕ ፡ ኀበ ፡ ዝንቱ ፡ ቃሉ ፡ ለልዑል ፡ ዘይቤ ፡ በእንተ ፡ አዳም ፡ ኢይሤኒ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ አዳም ፡ ባሕቲቱ ፡ ንግበር ፡ሎቱ ፡ቢጸ ፡ ዘይረድኦ ።

፰፻፸፱ ወመፍቅድ ፡ ቀዳማዊ ፡ ዘአውስቦ ፡ በእንተ ፡ ወሊደ ፡ ውሉድ ፡ ወአብጥሎ ፡ ፍትወት ፡ ወተረድኦ ፡ አው ፡ ተጋብኦ ። ወአውስቦሰ ፡ በአምሳል ፡ ኀበ ፡ ጥንተ ፡ ነገድ ፡ ይሔር ፡ ኀቤሃ ፡ በጥንተ ፡ ሕግ ፡ ዘቀደመ ፡ ተነግሮቱ ፡ ወውእቱኒ ፡

## አንቀጽ ፡ ፳፭ ።

ስለ ፡ አስተጫጨትና ፡ ማጫ ፡ ስለመስጠት ፡ ስለማግባትና ፡ ከግቢ ፡ በኋላ ፡ ስለሚደረገው ።

፰፻፸፯ እርሱም ፡ ስድስት ፡ ምዕራፎች ፡ አሉት ። መጀመሪያው ፡ ምዕራፍ ፡ ስለጋብቻ ፡ ከመናገራችን ፡ በፊት ፡ የሚቀድመውን ፡ ነገር ፡ ልንናገር ፡ ይገባናል ። ለመጀመሪያው ፡ ፈቃድ ፡ ሁለት ፡ ሥራዎች ፡ አሉትና ። ከሁለቱ ፡ አንዱ ፡ ዘር ፡ ለመተካት ፡ ልጅ ፡ መውለድ ፡ ነው ። ለቀደሙ ፡ አያቶች ፡ ብዙ ፡ ተባዙ ፡ ያላቸው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደዚህ ፡ ይመራል ። (ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፳፰) ። ይኸውም ፡ ልጅ ፡ ለመውለድ ፡ ያለሩካቤ ፡ አይፈጸምም ።

፰፻፸፰ ዳግመኛም ፡ በሰው ፡ በእንስሳዊ ፡ ባሕርዩ ፡ የፈቲው ፡ ፆር ፡ በጸናችበት ፡ ጊዜ ፡ ከእርሱ ፡ የሚገኝለት ፡ የሩካቤ ፡ ፍላጎት ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ከሁለት ፡ ይከፈላል ። አንዱ ፡ ልጅ ፡ ለመውለድ ፡ በሚገናኙበት ፡ ጊዜ ፡ ፈቃድን ፡ መስጠት ፡ ነው ። ሁለተኛውም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ድካምን ፡ ለማቅለል ፡ አንዱ ፡ ለአንዱ ፡ የሚያደርገው ፡ በተጋቡት ፡ መካከል ፡ የሚደረግ ፡ መረዳዳት ፡ ነው ። ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአዳም ፡ ጓደኛ ፡ እንፍጠርለት ፡ እንጂ ፡ ብቻውን ፡ ሊሆን ፡ አይገባም ፡ ብሎ ፡ የተናገረውም ፡ ቃል ፡ ወደዚህ ፡ ይመራል ። (ዘፍ ፡ ፪ ፡ ፲፰ ።)

፰፻፸፱ ጋብቻን ፡ ያስፈለገው ፡ መጀመሪያው ፡ ነገር ፡ ልጅን ፡ ለመውለድ ፡ ፍትወትን ፡ ለማራቅ ፡ ለመረዳዳትና ፡ አንድ ፡ ለመሆን ፡ ነው ። አስቀድሞ ፡ በተነገረው ፡ በአራቱ ፡ ሥርዓት ፡ (ዘፍ ፡ ፪ ፡ ፳) ። ዳግመኛም ፡ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ በተነ

ካዕበ ፡ ዘይኀሪዊ ፡ ሕግ ፡ ዘተናገረ ፡ በፍጻሜሁ ፡ ለዝንቱ ፡ ዓስም ፡ ኀበ ፲ቱ ፡ አክፋል ፡ ይትከፈል ።

፫፻፴፱ ክፍል ፡ ቀዳማዊ ፡ ሶበ ፡ ኮነ ፡ ውዕየት ፡ ዘፍትወት ፡ በብዙኀን ፡ ዘያወድቅ ፡ ውስተ ፡ ተዓድዎ ፡ ሕግ ፡ ወአውሰቦስ ፡ በአርአያ ፡ ከመዝ ፡ ውእቱ ፡ መፍትው ፡ ይሑር ፡ ኀቤሃ ፡ ወይመርሕ ፡ በእንቲአሁ ፡ ቃለ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ዘይቤ ፡ በመልእክቱ ፡ ለሰብአ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ቀዳማዊ ፡ ዘ፯ቱ ። "እቤሎሙ ፡ ዘንተ ፡ ለእለ ፡ እልቦሙ ፡ አንስት ፡ ወለመበለታት ፡ ሠናይ ፡ ሎሙ ፡ እመ ፡ ነበሩ ፡ ከማየ ፡ ወእመ ፡ ኢይክሉ ፡ ተዓግሦ ፡ ለያውስቡ ፡ እስመ ፡ ሠናይ ፡ አውስቦ ፡ እምዋዕዩ ፡ በፍትወት" ። ወበብሂሎቱኒ ፡ በእንተ ፡ መበለታት ፡ ዐዋድያት ፡ በመልእክቱ ፡ ኀበ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ቀዳማዊ ፡ ፭ቱ ፡ "አንስ ፡ እፈቅድ ፡ ከመ ፡ ይትዋሰባ ፡ ውርዝዋት ፡ እምኔሆን ፡ ወይለዳ ፡ ውሉደ ፡ ወይመግባ ፡ አብያቲሆን ፡ ከመ ፡ ኢይርከብ ፡ ጸላኢ ፡ ምንተኒ ፡ ምክንያተ ፡ ስላቅ" ።

፫፻፵ ወዳግምኒ ፡ አውሰቦስ ፡ ያደሉ ፡ ኀዲጎታ ፡ ለዘይትከሀሎ ፡ መዊዐ ፡ ፍትወታት ፡ እመ ፡ አኮ ፡ በእንተ ፡ ሂሩተ ፡ ቱሰሕት ፡ አው ፡ በእንተ ፡ ሥነ ፡ ልማዳቲሁ ፡ አው ፡ በእንተ ፡ ኂሩተ ፡ ተመስሎቱ ። ወይመርሕ ፡ ኀበ ፡ ዝንቱ ፡ ቃለ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ለሰብአ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ቀዳማዊ ፡ ፯ቱ ፡ " በእንተ ፡ ግብርሰ ፡ ዘጸሐፍክሙ፡ ሊተ ፡ በእንቲአሃ ፡ ሠናይ ፡ ውእቱ ፡ ለብእሲ ፡ ኢቀሪበ ፡ አንስት ፡ ወባሕቱ ፡ ከመ ፡ ኢይዘምዉ ፡ ይንበር ፡ ብእሲ ፡ ምስለ ፡ ብእሲቱ ፡ ወብእሲትኒ ፡ ትንበር ፡ ምስለ ፡ ምታ ። ወእብል ፡ ዘንተ ፡ ከመ ፡ ዘይትከሀል ፡ ለድኩማን ፡ አኮ ፡ በትእዛዝ ፡ ምቱር ። ወአንሰ ፡ እፈቅድ ፡ ከመ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ይኩን ፡ ከማየ ፡ በንጽሕ ፡ ወባሕቱ ፡ በከመ ፡ ከፈሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምኒ ፡ ጸጋሁ ፡ ወቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ ለዘከመዝ ፡ ጸጋሁ ፡ ወቦ ፡ ለዘከመዝ ፡ ሀብቱ ። ወበእንተ ፡ ድንግልናሰ ፡ አልቦ ፡ በኀቤየ ፡ ትእዛዝ ፡ በእንቲአሃ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወባሕቱ ፡ እመክር ፡ በእንቲአሃ ፡ ከመ ፡ ብእሲ ፡ ዘጸገዎ ፡ እግዚአብ



ገረው ፡ በወንጌል ፡ ሥርዓት ፡ (ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፭) ። ጥንተ ፡ ነገድን ፡ በመምሰል ፡ ወደርሷ ፡ ይሄድ ፡ ዘንድ ፡ የሚደረግ ፡ ግቢ ፡ ከ፲ ፡ ይከፈላል ።

፫፻፴፱ መጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ በፈቲው ፡ ፆር ፡ ብዙዎቹን ፡ ሕግ ፡ በማፍረስ ፡ ውስጥ ፡ የምትጥል ፡ በሆነች ፡ ጊዜ ፡ ወንዱ ፡ ወደሴቲቱ ፡ መሄድ ፡ እንዲገባው ፡ ይናገራል ። በአምሳል ፡ የሚደረገው ፡ ግቢ ፡ እንደዚህ ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ ለቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ በጻፈው ፡ በመጀመሪያው ፡ መልእክቱ ፡ በ፯ኛው ፡ ክፍል ፡ የተናገረው ፡ ወደዚህ ፡ ይመራል ። እንዲህም ፡ አላቸው ። ሚስት ፡ የሌላቸው ፡ ወንዶችና ፡ ባል ፡ የሌላቸው ፡ ሴቶች ፡ እንደእኔ ፡ ሆነው ፡ ቢኖሩ ፡ ይሻላቸዋል ። መታገሥ ፡ ባይችሉ ፡ ግን ፡ ያግቡ በፈቲው ፡ ፆር ፡ ከመቃጠል ፡ ማግባት ፡ ይሻላልና ፡ (፩ኛ ፡ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፰ -፱) ። ባል ፡ ስለሌላቸው ፡ ዘዋሪዎች ፡ ሴቶችም ፡ ስጢሞቴዎስ ፡ በላከው ፡ መልእክት ፡ በ፭ኛው ፡ ክፍል ፡ ወጣቶች ፡ ሴቶች ፡ እንዲያገቡ ፡ ልጆችንም ፡ እንዲወልዱ ፡ ቤታቸውንም ፡ እንዲያስተዳድሩ ፡ እወዳለሁ ። ጠላት ፡ የመሳለቂያ ፡ ምክንያትን ፡ ምንም ፡ እንዳያገኝ ፡ በማለቱ ፡ አስረዳ ። (፩ኛ ፡ ጢሞ ፡ ፭ ፡ ፲) ።

፫፻፵ ሁለተኛውም ፡ ክፍል ፡ ፀቱ ፡ ባሕርያት ፡ ስለመስማማታቸው ፡ ወይም ፡ በጎ ፡ ልማድ ፡ ስላለው ፡ ወይም ፡ ስለምባሌው ፡ መልካምነት ፡ የፈቲውን ፆር ፡ ድል ፡ መንሣት ፡ ለሚቻለው ፡ ሰው ፡ አለ ማግባት ፡ እንዲገባ ፡ ይናገራል ። ወደዚህም ፡ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ ለቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ በመጀመሪያ ፡ መልእክቱ ፡ በ፯ኛው ፡ ክፍል ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ይመራል ። ስለጻፋችሁልኝ ፡ ሥራስ ፡ ሰው ፡ ወደሴቶች ፡ ባይቀርብ ፡ መልካም ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ እንዳይሰስኑ ፡ ወንድ ፡ ከሚስቱ ፡ ጋር ፡ ይኑር ። ሴትም ፡ ከባሏ ፡ ጋር ፡ ትኑር ። ይህንም ፡ ለደካሞች ፡ እንደሚቻል ፡ እናገራለሁ ። በቍርጥ ፡ ትእዛዝ ፡ አይደለም ። እኔ ፡ ግን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በንጽሕና ፡ እንደኔ ፡ ሊሆን ፡ እወዳለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ከጸጋው ፡ እንዳደለው ፡ ነው ። ከእነርሱም ፡ ስጦታው ፡ እንደዚህ ፡ የሆነ ፡ አለ ። ሀብቱ ፡ እንደዚህ ፡ የሆነም ፡ አለ ። ስለ ፡ ድንግልና ፡ ግን ፡ በእኔ ዘንድ ፡ ስለርሷ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ የለም ። ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ያደለው ፡

ሐር ፡ ይኩን ፡ ምእመነ ። ወባሕቱ ፡ እትሐዘብ ፡ ከመ ፡ ዝንቱ ፡ ግብር ፡ ሠናይ ፡ በእንተ ፡ መከራ፡ ዘመን ፡ ወይኄይሶ ፡ ለብእሲ ፡ ይንበር ፡ ከመዝ። ወአመ ፡ ኮንከ ፡ አ ፡ ብእሲ ፡ እሡረ ፡ በብእሲ ትከ ፡ ኢትኅሥሥ ፡ ተፈልጦታ ፡ ወእመሰ ፡ ኮንከ ፡ ዘኢትፈቅድ ፡ ብእሲተ ፡ ኢትኅሥሥ ፡ ኪያሃ ፡ እስመ ፡ ይከውን ፡ ምንዳቤ ፡ ወመከራ ፡ በውስተ ፡ ሥጋ ፡ ለእለ ፡ ሀለዉ ፡ ከመዝ ። ወባሕቱ ፡ አንሰ ፡ አምህከክሙ ፡ ወእብለክሙ ፡ ዘንተ ፡ አ ፡ አኃውየ ፡ እስመ ፡ መዋዕል ፡ ናሁ ፡ ቀርበ ። ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ እፈቅድ ፡ ዘእንበለ ፡ ኀዘን ፡ ከመ ፡ ተሀልዉ ። እስመ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ብእሲት ፡ ይሔሊ ፡ ለግብረ ፡ እግዚኡ ዘከመ ፡ እፎ ፡ ያሠምሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወዘሰ ፡ ቦቱ ፡ ብእሲት ፡ ይሔሊ ፡ ለግብረ ፡ ዓለም ፡ ዘከመ ፡ እፎ ፡ ያሠምራ ፡ ለብእሲቱ ።

፰፻፴፩ ወዝንቱ ፡ ይትከፈል ፡ እስመ ፡ ማእከለ ፡ ዘያወስብ ፡ ወማእከለ ፡ ድንግል ፡ ሀሎ ፡ ፍልጠት ፡ ዕዉቅ ፡ እስመ ፡ እመ ፡ ኢኮነት ፡ ብእሲት ፡ ለብእሲ ፡ ትሔሊ ፡ በእንተ ፡ ዘያቀርባ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ትኩን ፡ ንጽሕተ ፡ በሥጋሃ ፡ ወነፍሳ ፡ ወእንተሰ ፡ ላቲ ፡ ምት ፡ ትሔሊ ፡ ለግብረ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ዘከመ ፡ እፎ ፡ ታሠምሮ ፡ ለምታ ። ወአንሰ ፡ እቤ ፡ ዘንተ ፡ ለበቍዓትክሙ ፡ ወአኮ ፡ ከመ ፡ አሥግርክሙ ፡ ለተኀንቆ ፡ ዳእሙ ፡ ከመ ፡ ትጽሐቁ ፡ ዘልፈ ፡ ለቀሪብ ፡ ኀበ ፡ ለግዚእክሙ ፡ በአርአያ ፡ ሠናይ ፡ እንዘ ፡ ኢታስተሐምሙ ፡ ለግብረ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ። ወለእመቦ ፡ ብእሲ ፡ ዘይሔሊ ፡ ከመ ፡ ይከውኖ ፡ ሰላቀ ፡ ወየኀፍር ፡ በእንተ ፡ ድንግል ናሁ ፡ እስመ ፡ ኀለፎ ፡ ጊዜ ፡ አውስቦ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ያውስብ ፡ ወይግበር ፡ ወኢኮነ ፡ መአብሰ ፡ ወለእመሰ ፡ መተረ ፡ በሕሊናሁ ፡ ከመ ፡ ይዕቀብ ድንግልናሁ ፡ ኢያገብሮ ፡ መኑሂ ፡ ከመ ፡ ያዕሉ፡ እስመ ፡ ፈድፋደ ፡ ሠናየ ፡ ግብረ ፡ ገብረ ። ወኵሉ ፡ ዘይሜጡ ፡ ድንግልናሁ ፡ ለአውስቦ ፡ ሠናየ ፡ ገብረ ፡ ወዘሰ ፡ ኢመጠወ ፡ ድንግልናሁ ፡ ለአውስቦ ፡ እንተ ፡ ትኄይስ ፡ ፈድፋደ ፡ ሠናየ ፡ ገብረ" ።

፰፻፴፪ ወሐዋርያኒ ፡ ተለወ ፡ ዘንተ ፡ ከመ ፡ ቃለ ፡ እግዚእነ ፡ ዘይቤ ፡ በወንጌል ፡ ቅዱስ ፡ ዘማቴዎስ ፡ ዘ፲ወ፺ቱ ፡ በተፍጻሜቱ ፡ ምዕራፉ ፡ ዘይቤ ፡ እስመ ፡ ቦ ፡ ሕጽዋን ፡ እለ ፡ ሐጸዉ ፡ ርእሶሙ ፡



ሰው ፡ የታመነ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ስለርሷ ፡ እመክራለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ዘመን ፡ መከራ ፡ ይህ ፡ ግብር ፡ መልካም ፡ እንደሆነ ፡ እጠራጠራለሁ ። ለሰው ፡ እንደዚህ ፡ ቢኖር ፡ ይሻለዋል ። ሰው ፡ ሆይ ፡ በሚስትህ ፡ የታሠርህ ፡ ብትሆን ፡ ልትለያት ፡ አትሻ ። ሴትን ፡ የማትወድ ፡ ከሆንክ ፡ ግን ፡ እርሷን ፡ አትሻ ። በእንደዚህ ፡ ላሉ ፡ ሰዎች ፡ በሥጋ ፡ ጭንቅ ፡ መከራ ፡ ይሆናልና ። ነገር ፡ ግን ፡ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡ ስለራራሁላችሁ፡ ይህን ፡ እልኋችሁ ። እነሆ ፡ ዘመን ፡ ቀርቧልና ። ስለዚህ ፡ ያለኀዘን ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ፡ እወዳለሁ ። ሚስት ፡ የሌለችው ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንዴት ፡ ደስ ፡ እንደሚያሰኘው ፡ ለጌታው ፡ ሥራ ፡ ያስባልና ። ሚስት ፡ ያለችው ፡ ግን ፡ ሚስቱን ፡ እንዴት ፡ ደስ ፡ እንደሚያሰኛት ፡ ለዓለም ፡ ሥራ ፡ ያስባል ።

፰፻፴፩ ይኸም ፡ ይከፈላል ፡ በሚያገባ ፡ መካከልና ፡ በድንግል ፡ መካከል ፡ የታወቀ ፡ ልዩነት ፡ አለና ። ሴት ፡ ለወንድ ፡ ካልሆነች ፡ በሥጋዋም ፡ በነፍሷም ፡ የነጻች ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለሚያቀርባት ፡ ነገር ፡ ታስባለችና ። ባል ፡ ያላት ፡ ሴት ፡ ግን ፡ ባሏን ፡ እንዴት ፡ ደስ ፡ እንደምታሰኘው ፡ ለዚህ ፡ ዓለም ፡ ሥራ ፡ ታስባለች ። በችግር ፡ ላጠምዳችሁ ፡ አይደለም። ለዚህ ፡ ዓለም ፡ ሥራ ፡ ሳታስቡ ፡ በመልካም ፡ አርአያ ፡ ወደጌታችሁ ፡ ለመቅረብ ፡ ዘወትር ፡ ትተጉ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ። የሚያገባበት ፡ ጊዜ ፡ ስለአለፈበት ፡ መዘባበቻ ፡ እንደሚሆንበት ፡ የሚያስብ ፡ ስለድንግልናውም ፡ የሚያፍር ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ እንዲያገባ ፡ ማድረግ ፡ ይገባዋል ። በደለኛም ፡ አይደለም ። ድንግልናውን ፡ ይጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ በአሳቡ ፡ ቢቆርጥ ፡ ግን ፡ ቃሉን ፡ እንዲለውጥ ፡ ማንም ፡ አያገብረው ፡ እጅግ ፡ ያማረ ፡ ሥራ ፡ ሠርቷልና ። ድንግልናውን ፡ ለማግባት ፡ የሰጠም ፡ ሁሉ ፡ መልካም ፡ አደረገ ። ድንግልናውን ፡ ለማግባት ፡ ያልሰጠ ፡ ግን ፡ እጅግ ፡ የበለጠች ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ ሠራ ። (፩ኛ ፡ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፩ - ፴፱) ።

፰፻፴፪ ሐዋርያውም ፡ ጌታችን ፡ ማቴዎስ ፡ በጻፈው ፡ በቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ በ፲፺ኛው ፡ ምዕራፍ ፡ መጨረሻ ፡ ስለመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ብለው ፡ ራሳቸውን ፡ የሰለቡ ፡ አሉና ፡ ሊሸከም ፡ የሚችል ፡

በእንተ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ወዘይክል ፡ ከመ ፡ ይፁር ፡ ለይፁር ፡፡ ወዘንተ ፡ ይቤ ፡ በእ ንተ ፡ ተሠጥዎተ ፡ ቃሎሙ ፡ ለእርድእት ፡ ሶበ ፡ ይቤልዎ ፡ እመሰ ፡ ከመዝ ፡ ሥርዓተ ፡ ብእሲ ፡ ምስለ ፡ ብእሲቱ ፡ ኢርቱዕ ፡ ከመ ፡ ያውስቡ ፡፡ ወኢይቤ ፡ እግዚእነ ፡ በዝንቱ ፡ ቃል ፡ በእንተ ፡ መቲረ ፡ አባለ ፡ ዘርእ ፡ እስመ ፡ ዝንቱስ ፡ ያር ኅቅ ፡ እመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ በከመ ፡ ቀደመ ፡ ገሥጾተ ፡ ዝንቱ ፡ ግብር ፡ በኀበ ፡ ተነግረ ፡ ለተ ከልአ ፡ እምኔሁ ፡ ዘንቡር ፡ ቅድመ ፡፡ አላ ፡ ይቤ ፡ በእንተ ፡ መቲረ ፡ ገቢረ ፡ ፍጻሜ ፡ ለመቲረ ፡ መፍቅዳት ፡ ለበጺሕ ፡ ኀበ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማ ያት ፡፡ ወዓዲ ፡ እምነ ፡ ቃሉ ፡ ዘንቡር ፡ በብሥ ራተ ፡ ማቴዎስ ፡ ወማርቆስ ፡ ወሉቃስ ፡ "እሜን እሜን ፡ እብለክሙ ፡ እልቦ ፡ መኑሂ ፡ ዘየኀድግ፡ ብእሲቶ ፡ በእንተ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ወኢይነሥእ ፡ ህየንተ ፡ ዝንቱ ፡ ምክዕቢተ ፡ ብዙኀ ፡ በዝ ፡ ዓለም ፡ ወበዘይመጽእኒ ፡ ሕይ ወተ ፡ ዘለዓለም" ፡፡

ይሸከም ፡ ብሎ ፡ እንደተናገረ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ተከተለ ፡፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ የወንድ ፡ ሥርዓት ፡ ከሚስቱ ፡ ጋር ፡ እንደዚህ ፡ ከሆነ ፡ ሊያገቡ ፡ አይገባም ፡ ባሉት ፡ ጊዜ ፡ ስለጥያቄያቸው ፡ መልስ ፡ ይህን ፡ ተናገረ ፡፡ (ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፲ - ፲፫)፡፡ ጌታችን ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ እባለ ፡ ዘርእን ፡ ስለመ ቁረጥ ፡ አልተናገረም ፡፡ ይህ ፡ ከመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ያርቃልና ፡፡ ከእርሱ ፡ ለመከልከል ፡ አስቀድሞ ፡ በተነገረው ፡ አንቀጽ ፡ ይህ ፡ ሥራ ፡ አስቀድሞ ፡ እንደተከለከለ ፡፡ ፈቃድን ፡ በመ ተው ፡ ወደመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ለመድረስ ፡ ማድረግን ፡ ፈጽሞ ፡ ስለመተው ፡ ተናገረ ፡ እንጂ ፡፡ ዳግመኛም ፡ ስለመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ብሎ ፡ ሚስቱን ፡ የተወ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ስለዚህ ፡ ፈንታ ፡ ብዙ ፡ ሰጥፍ ፡ ድርብ ፡ በሚመጣውም ፡ ዓለም ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወ ትን ፡ የማያገኝ ፡ የለም ፡ ብዬ ፡ በእውነት ፡ እነ ግራችኋለሁ ፡ ብሎ ፡ በማቴዎስ ፡ በማርቆስ ፡ በሉቃስ ፡ ወንጌል ፡ ከተጻፈው ፡ ቃሉ ፡ የተነሣ ፡ ነው ፡፡ (ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ጽ፱ ፡፡ ማር ፡ ፲ ፡ ጽ፱) ፡፡

፰፻፴፫ ወሣልስኒ ፡ አውስቦስ ፡ ብዉሕ ፡ በከመ ፡ ርኢነ ፡ ለዘሀለወ ፡ በክልኤቱ ፡ ፍናዋት ፡ ቀዳማውያን ፡ ይትዐወቅ ፡ ከመ ፡ ኢየዐይ ፡ በእሳተ ፡ ፍትወት ፡ ወለዘኢኮነ ፡ ዕሩፈ ፡ እምኔሃ ፡፡ ወይመርሕ ፡ በእ ንተ ፡ ዝንቱ ፡ ቃለ ፡ ሐዋርያ ፡ ዘይቤ ፡ ዘ፰ቱ ፡ ወለእመ ፡ ፈቀድከ ፡ ከመ ፡ ታውስብ ፡ እኮ ፡ ዝንቱ ፡ አበሳ ፡ ወለእመ ፡ ተወሰበት ፡ ድንግል ፡ ለብእሲ ፡ እኮ ፡ እበሳ ፡ ላዕሌሃ ፡ ካሰበ ፡፡ ሰብ ፡ ፲ወ፩ዱ ፡ ክቡር ፡ ውእቱ ፡ አውስቦ ፡ በኵሉሂ ፡ ወለምስካበሙኒ ፡ እልቦቱ ፡ ስዕበት ፡፡

፰፻፴፫ ሦስተኛውም ፡ ማግባት ፡ ግን ፡ እኛ ፡ እንዳየ ነው ፡ በቀደሙት ፡ ሁለት ፡ ግብራት ፡ ላለ ፡ ሰው ፡ የተፈቀደ ፡ ነው ፡፡ ከእርሷ ፡ ያረፈ ፡ ያል ሆነ ፡ ሰው ፡ በፈቲው ፡ እሳት ፡ እንዳይቃጠል ፡ እንዲሆን ፡ ይታወቃል ፡፡ ስለዚህም ፡ ሐዋርያው ፡ በ፰ኛው ፡ ክፍል ፡ ልታገባ ፡ ብትወድ ፡ ይህ ፡ በደል ፡ አይደለም ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ይመራል ፡፡ ዳግመኛም ፡ ድንግል ፡ ባል ፡ ብታገባ ፡ በደል ፡ አይሆንባትም ፡፡ (፩ኛ ፡ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ጽ፰) ፡፡ ዕብ ፡ ፲፩ ፡፡ ጋብቻ ፡ ሁልጊዜ ፡ የከበረ ፡ ነው ፡ ለመኝታ ቸውም ፡ ርኵሰት ፡ የለበትም ፡፡ (ዕብ ፡ ፲፫ ፡ ፬) ፡፡

፰፻፴፬ በሰ ፡ ፳ቱ ፡ ወአውስቦሰ ፡ እምድኅረ ፡ በዕዐ ፡ ድንግልናሁ ፡ ኀፍረት ፡ ውእቱ ፡፡ ዘዕንቀራ ፡ ፲ወ፰ቱ ፡ ወኵሉ ፡ ዘበዕዐ ፡ ከመ ፡ ይዕቀብ ፡ ድን ግልናሁ ፡ ይፈጸም ፡ ፈቃዳቲሁ ፡ ወእመ ፡ እኮ ፡ ይከውን ፡ ፍትሑ ፡ ከመ ፡ ዘእውሰበ ፡ ፪ተ ፡ እን ስተ ፡፡ ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ቃል ፡ ዘንቤ ፡ እስመ ፡ እውስቦ ፡ ቀዳማዊ ፡ ዘበእሐቲ ፡ ብእሲት ፡ ወአ ውስቦስ ፡ ዳግማዊት ፡ ካልእት ፡ ተሐፅፅ ፡ እምቀ ዳማዊት ፡ ወለሃቲ ፡ ተሠርዐ ፡ በቀኖናት ፡ ከመ፡ ኢትኩን ፡ ላቲ ፡ በረከተ ፡ ተክሊል ፡ አላ ፡ ይግ በሩ ፡ ጸሎተ ፡ እስተሥርዮ ፡፡

፰፻፴፬ በሰ ፡ ፳ ፡፡ ድንግልናዉን ፡ ከተሳለ ፡ በኋላ ፡ ማግ ባት ፡ ኀፍረት ፡ ነው ፡፡ ዕንቀራ ፡ ፲፰ ፡፡ ድንግል ናዉን ፡ ይጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ የተሳለ ፡ ሁሉ ፡ ፈቃ ዱን ፡ ይፈጽም ፡፡ ባይፈጽም ፡ ግን ፡ ፍርዱ ፡ ሁለት ፡ (ሚስት) ፡ ሴቶች ፡ እንዳገባ ፡ ይሆናል'፡፡ የተናገርነውም ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡ መጀመሪ ያው ፡ ግቢ ፡ በአንዲት ፡ ሴት ፡ የሚሆነው ፡ ነውና ፡፡ ከሌላይቱ ፡ ጋራ ፡ የምትሆነው ፡ ሁለተ ኛዪቱ ፡ ግቢ ፡ ግን ፡ ከፊተኛይቱ ፡ ታንሣለችና ፡ ለዚች ፡ የማስተሥርያ ፡ ጸሎት ፡ ያድርጉ ፡ እንጂ ፡ ተክሊል ፡ እንዳይደርስላት ፡ በሕግ ፡ ተጻፈ ፡፡

አንቀጽ ፡ ፹፱ ።

፳፻፴፭ በስ ፡ ፵ወ፫ቱ ፡ ወእመሰኬ ፡ ዖፈ መንጢጥ ፡ ዘኢ
ነባቢ ፡ ይትገኑሥ ፡ እምአውስቦ ፡ ዳግማዊ ፡
እፎ ፡ እንከ ፡ ፈድፋደ ፡ ይደሉ ፡ ለእንስሳ ፡
ነባቢ ። ወበእንተ ፡ ዘኢኮነት ፡ ብውሕተ ፡ ወበ
እንተ ፡ ዝንቱ ፡ ፍና ፡ ይደሉ ፡ ዐቂበ ፡ ዛቲ ፡
ሕግ ። እለመ ፡ ይእቲ ፡ ታወርዶሙ ፡ ለከቡራን ፡
እምክብሮሙ ፡ ዘውእቶሙ ፡ ካህናት ፡ ወይእቲ ፡
ሎሙ ፡ ትከውን ፡ ምንንተ ።

፳፻፴፮ ወአውስቦሰ ፡ ሣልስ ፡ ምኑን ፡ ውእቱ ፡ ወአልቦ፡
ዘነበሩ ፡ እምድኅረዝ ፡ አውስቦ ፡ ሕጋዊ ። ወተ
ጋብአሂ ፡ ማእከለ ፡ አውስቦ ፡ ዳግማዊ ፡ እው ፡
ዘይበዝኅ ፡ ኢይደሉ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ዝሙት ፡
ክሡት ፡ ዘተነግረ ፡ ወይትከሠት ፡ እምዘ ፡ ተዘ
ክረ ፡ በእንተ ፡ ዘይትፈቀድ ፡ ከዊነ ፡ አውስቦ ።
እስመ ፡ እምድኅረ ፡ ኩነቱ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ኢይ
ኩን ፡ ተደምሮቱ ፡ ዘእሙር ፡ ዘእንበለ ፡ ለእስ
ስሎ ፡ ሕማመ ፡ ፍትወት ፡ እው ፡ ለኀሣሠ ፡
ዘርእ ፡ ዘያሠምሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወዘይትቀ
ነይ ፡ ሎቱ ፡ ወይትከሠት ፡ ካዕበ ፡ ከመ ፡ ኢይ
ደሉ ፡ ፍኅረት ፡ ሶበ ፡ ተዐውቀ ፡ ግእዙ ፡ እም
ድኅረ ፡ ግብሩ ፡ እምቴሳሔሁ ፡ ወልባዌሁ ፡
በእምግነ ፡ መዋዕሉ ፡ ትሕዝብተ ፡ ዘይከውን ፡
እምኔሁ ፡ እምድኅረ ፡ ምንዳቤ ፡ ፍትወታት ፡
ወተመውዖ ፡ እምኔሃ ፡ እው ፡ እምአጥፍአታ ፡
ወዘይደሉ ፡ እንዘ ፡ ።

፳፻፴፯ ወዘይበዝኅስ ፡ ነገር ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ አንቀጽ ፡
እምቀኖናት ፡ እሙራት ፡ ዘአብጥሊሳት ፡ በአና
ቅጽ ፡ ቀዳማውያን ፡ ዘ፲ወ፩ዱ ። ወአእምር ፡
ከመ ፡ መፍቅዳተ ፡ አውስቦ ፡ ፫ቱ ፡ እሙንቱ ፡
እለ ፡ ዝከራን ፡ ዘውእቶሙ ፡ ከመ ፡ ግብረ ፡
ፈጣሪ ፡ ጠቢብ ፡ ልዑል ፡ ወእምእለ ፡ ተሰውዎ ፡
እግብርቲሁ ፡ ወኢረክብነ ፡ ፩ደ ፡ እምእሉ ፡ ዘይ
ፈቅዳ ፡ ለሕገ ፡ አውስቦ ፡ ዘእንበለ ፡ ለከዊነ ፡
ዘርእ ፡ ባሕቲቱ ።

፳፻፴፰ ወእመ ፡ ኮነ ፡ ብእሲ ፡ ዘይደመር ፡ ምስለ ፡ ብእ
ሲቱ ፡ እምድኅረ ፡ ተከሥተ ፡ ፅንሳ ፡ ወዝንቱ ፡
ኢርቱዕ ፡ ወኢብውሕ ፡ ሎቱ ፡ ወበሂ ፡ ይፈቅዳ ፡
ኢይፈቅድ ፡ ኪያሃ ፡ ዘእንበለ ፡ ተራድኦ ፡ ባሕ
ቲቱ ። ወእመ ፡ ኮነ ፡ ግሙራ ፡ ዕጢቀ ፡ ዘይወ
ድቅ ፡ ዘኢኮነ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቦቱ ፡ ዘንተ ፡ ዜና ፡
ይስማዕ ፡ ውእቱ ።

፳፻፴፱ ወእውስቦሰ ፡ በአምጣነ ፡ ፈቃዶሙ ፡ ለእለ ፡

ስለ ፡ ጋብቻ ።

፳፻፴፭ በስ ፡ ፵፫ ። የማይናገር ፡ ዖፈ ፡ መንጢጥ ፡ ከሁ
ለተኛ ፡ ግቢ ፡ የሚርቅ ፡ ከሆነ ፡ ለሚናገር ፡
እንስሳ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይገባው ፡ ይሆን ? ። ስለ
ዚህም ፡ ነገር ፡ ያልተፈቀደች ፡ ስለሆነች ፡ ያችን
ሕግ ፡ መጠበቅ ፡ ይገባል ። ያህች ፡ ክቡራንን ፡
ከክብራቸው ፡ ታዋርዳቸዋለችና ። እነዚህም ፡
ካህናት ፡ ናቸው ። ይህችውም ፡ ለእነርሱ ፡ የተ
ናቀች ፡ ትሆናለች ።(

፳፻፴፮ ፫ኛ ፡ ግቢ ፡ ግን ፡ የተናቀ ፡ ነው ። ከዚህም ፡
በላይ ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ ሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ የለም ።
በ፪ኛው ፡ ግቢ ፡ ወይም ፡ በሚበዛ ፡ (በ፫ኛ) ፡
ግቢ ፡ መሰብሰብ ፡ እይገባም ። ይህ ፡ የተነገረ ፡
ግልጥ ፡ ዝሙት ፡ ነውና ። የጋብቻ ፡ እኳንን ፡
ስለሚሻ ፡ ከተነገረው ፡ ቃል ፡ የተነሣ ፡ ይገለ
ጻል ። ይህ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ የታወቀ ፡ ግንኙነቱ፡
የፈቲውን ፡ ዖር ፡ ለማራቅ ፡ ወይም ፡ እግዚአብ
ሔርን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘው ፡ ለእርሱም ፡ የሚገ
ዛ ፡ ልጅ ፡ ለመውለድ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ እን
ዳይሆን ፡ ይገባልና ። ዳግመኛም ፡ በፈቲው ፡
ከመቸገር ፡ ከእርጊም ፡ ድል ፡ ከመነሣት ፡
ወይም ፡ እርሷን ፡ ከማጥፋትና ፡ ከሚገባ ፡ እር
ሷን ፡ ከመያዝ ፡ በኋላ ፡ ከርሱ ፡ የሚሆን ፡ ጥር
ጥርን ፡ እንደማሸነፉ ፡ መጠን ፡ ከጠባዩ ፡ ከእ
ሳቡ ፡ (ከእስተዋይነቱ) ፡ የተነሣ ፡ ከሠራው ፡
ሥራ ፡ በኋላ ፡ ጠባዩ ፡ በታወቀ ፡ ጊዜ ፡ ማጨት ፡
እንዳይገባ ፡ (ይታወቃል) ፡ ይገለጣል ።

፳፻፴፯ ከታወቁ ፡ ከአብጥሊስ ፡ መጻሕፍት ፡ በዚህ ፡
አንቀጽ ፡ ከተነገረው ፡ የሚበዛው ፡ ነገር ፡ በቀ
ደሙት ፡ በ፲፩ዱ ፡ አናቅጽ ፡ አለ ። የተነገሩ ፡
የጋብቻ ፡ ፈቃዶች ፡ ፫ ፡ እንደሆኑ ፡ እወቅ ። እነ
ርሱም ፡ ጠቢብ ፡ ልዑል ፡ የሆነ ፡ የፈጣሪ ፡ ሥራ
ዎች ፡ ናቸው ። ከተከተሉት ፡ አገልጋዮቹም ፡
ወገን ፡ ልጅ ፡ ለመውለድ ፡ ብቻ ፡ ካልሆነ ፡
በቀር ፡ የጋብቻን ፡ ሕግ ፡ የሚሻት ፡ አንድ ፡
ስንኳ ፡ አላገኘነም ።

፳፻፴፰ ፅንሷ ፡ ከታወቀ ፡ በኋላ ፡ ከሚስቱ ፡ ጋራ ፡ ሩካቤ
የሚያደርግ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ይህ ፡ አገባብ ፡ አይ
ደለም ። ለርሱም ፡ አይፈቀድለትም ። የሚሻ
ትም ፡ ለመረዳዳት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ እርሷን ፡
አይሻ ። አንድነት ፡ በሌለበት ፡ የሚወድቅ ፡
መሆኑ ፡ ፈጽሞ ፡ የታወቀ ፡ ቢሆን ፡ እርሱ ፡
ይህን ፡ ነገር ፡ ይስማ ።

፳፻፴፱ እንደ ፡ ወደዱ ፡ ማግባት ፡ ግን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡

አንቀጽ ፡ ፳፱ ።

ተርፋ ፡ ስብእ ፡ ዘለመሙ ፡ ባቲ ፡ መፍቅዳት ፡
ካልእት ፡ ወእሙንቱ ፡ ላዕለ ፡ ክፍላት ፡ ብዙ
ኃት ። ቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘይፈቅዳ ፡ ለአውስቦ ፡
በእንተ ፡ ጣዕመ ፡ ትፍግዕት ፡ ዘዝክርት ፡ ባሕ
ቲቱ ፡ ወኢይፈሊ ፡ ካልአ ፡ ዘእንበሌሃ ፡ ወኢ
ይኔጽር ፡ ኀበ ፡ እዋርዮ ፡ ዘርእ ፡ ወኢኀበ ፡ ረድ
ኤት ። አላ ፡ ቦ ፡ ዘይገብር ፡ እምከሊእ ፡ ፅንስ ፡
ወተፀንሶ ፡ እመኒ ፡ እመንገሌሁ ፡ አው ፡ እመን
ገለ ፡ ብእሲቱ ፡ ወተፀቅሮ ፡ በግብረ ፡ ተደምሮ ፡
ባቲ ፡ ወበነጽሮ ፡ ጣዕማት ፡ ባሕቲቱ ፡ ወይት
ዔገሥ ፡ በእንተ ፡ ሥነ ፡ ብእሲቱ ፡ ወሶበሂ ፡
ኮነት ፡ ነዳይተ ፡ አው ፡ ኅሡረ ፡ ኮነ፡ አዝማ
ዲሃ ፡ አላ ፡ ትማኒ ፡ መፍቅዶሙ ፡ ለእሉ ፡ እምድ
ኅረ ፡ ብዙኅ ፡ መዋዕል ። ወቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘይ
ፈቅድ ፡ አውስቦ ፡ በእንተ ፡ ብዝኅ ፡ ንዋይ ፡
አው ፡ በእንተ ፡ ዕበየ ፡ ክብር ፡ አው ፡ በእንተ ፡
ትምክህተ ፡ ዘመድ ፡ አው ፡ ለተደምሮ ። ወበእ
ንተ ፡ ዝንቱ ፡ ቦ ፡ ዘይትዔገሥ ፡ ሕሠመ ፡ ራእየ ፡
ብእሲቱ ፡ በእንተ ፡ ፍቅረ ፡ ንዋይ ፡ ወኢይዜክር
ኀጣረ ፡ አዝማዲሃ ። ወቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘየወ
ስብ ፡ በእንተ ፡ ክብረ ፡ አዝማዲሃ ፡ ወኢይዜ
ክር ፡ ንዴታ ፡ ወኢዕበየ ፡ አዝማዲሃ ። ወቦ ፡
እምኔሆሙ ፡ ዘያስተዋስቦ ፡ ጠቢብ ፡ አቡሁ ፡
አው ፡ መኰንን ፡ ዚአሁ ፡ አው ፡ ካልአኒሁ ፡
እንዘ ፡ ውእቱ ፡ ንኡስ ፡ በእንተ ፡ ተባድሮት ፡
ካልእ ፡ ኀበ ፡ ዘላቲ ፡ ሥነ ፡ ሠናይ ፡ አው ፡ በእ
ንተ ፡ ብዝኀ ፡ ንዋያ ፡ አው ፡ በእንተ ፡ አዝማ
ዲሃ ፡ አው ፡ በእንተ ፡ ትርሲታ ፡ አው ፡ በእ
ንተ ፡ ልባዊሃ ፡ ወሠምረ ፡ ከመ ፡ ኢታምሥጦ ።
ወእመ ፡ አኮ ፡ ቀዲም ፡ በእንተ ፡ ሁከተ ፡ ፍት
ወት ፡ ለሙስና ፡ ወለተፀቅቦ ፡ ፈሪሆ ፡ እምእ
ከየ ፡ ፈቃዳት ፡ ወእመ ፡ አኮ ፡ በእንተ ፡ ሁከተ ፡
ወላዲት ፡ ዘተሐውር ፡ ከመ ፡ ትትፈጣሕ ፡ ቦቱ ፡
ለእሐቲ ፡ ሰዓት ፡ ፈቂዶሙ ፡ ረቢነ ፡ ዝንቱ ፡
እምቅድመ ፡ ሞት ፡ አው ፡ እምቅድመ ፡ ንዴት፡
አው ፡ በእንተ ፡ አኀዝኖ ፡ ወተቃሕዎ ፡ አው ፡
መባሕት ። ወቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘይፈቅድ ፡ ዘር
እ ፡ በሕሊናሁ ፡ ሠናይት ፡ ወውእቱ ፡ ለእመ ፡
ይከውን ፡ ሎቱ ፡ ንዋይ ፡ ብዙኅ ፡ ወይፈቅድ ፡
ወልደ ፡ ዘይወርሶ ። ወኢንክል ፡ ንርከብ ፡
እምነ ፡ እሉ ክፍላት ፡ አለ ፡ ዝኩራን ፡ መፍቅደ ፡
ፍሉጠ ፡ ዘኢኮነ ፡ ክፍለ ፡ ትፍግዕት ፡ ወኢን
ክል ፡ ንርከብ ፡ ካልአ ፡ ክፍለ ፡ ዘኢኮነ ፡ ድሙረ

ስለ ፡ ጋብቻ ።

ፈቃድ ፡ ላላቸው ፡ ለቀሩት ፡ ሰዎች ፡ ነው ። እን
ዚህም ፡ በብዙዎች ፡ ክፍሎች ፡ ላይ ፡ ናቸው ።
ከእነርሱ ፡ ወገን ፡ ስለተነገረች ፡ የዝሙት ፡
ጣዕም ፡ ብቻ ፡ ጋብቻን ፡ የሚሻት ፡ አለ ። ከእ
ርሷም ፡ በቀር ፡ ሌላን ፡ አያስብም ። ልጅን ፡
ወይማግኘትና ፡ ወይመረዳዳትም ፡ አይመለ
ከትም ። በራሱ ፡ በኩልም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡
በሚስቱ ፡ በኩል ፡ ፅንስንና ፡ መፀነስን ፡ ከሚከ
ለክል ፡ ወገን ፡ የሚያደርግም ፡ አለ ። ጣዕመ ፡
ፍትወትን ፡ በመመልከትና ፡ ለሩካቤ ፡ ሥራ ፡
ብቻ ፡ በእርሷ ፡ ተቋጥሮ ፡ የሚኖርም ፡ አለ ።
ድኃ ፡ ብትሆንም ፡ ወይም ፡ ዘመዶቿ ፡ የተናቁ ፡
ቢሆኑ ፡ ስለሚስቱ ፡ ደም ፡ ግባት ፡ የሚታገሥ ፡
አለ ። ነገር ፡ ግን ፡ የእነዚህ ፡ እነዋሪቸው ፡
ከብዙ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ታምራለች ። ከእነር
ሱም ፡ ወገን ፡ ስለ ፡ ገንዘብ ፡ ብዛት ፡ ጋብ
ቻን ፡ የሚሻ ፡ አለ ። ወይም ፡ ስለ ፡ ክብር ፡ ገና
ንነት ፡ ወይም ፡ በዘመዶቿ ፡ ስለመመካት ፡
ወይም ፡ አብሮ ፡ ለመኖር ። ስለዚህም ፡ ስለገን
ዘብ ፡ ፍቅር ፡ የሚስቱን ፡ መልክ ፡ ጥፋነት ፡
የሚታገሥ ፡ አለ ። የዘመዶቿንም ፡ መዋረድ ፡
አያስብም ፡ ከእነርሱም ፡ ወገን ፡ ስለዘመዶቿ ፡
ክብር ፡ የሚያገባ ፡ አለ ። የእርሷን ፡ ችግርና ፡
የዘመዶቿን ፡ ዐላዋቂነት ፡ አያስብም ። ከእነ
ርሱም ፡ ብልህ ፡ አባቱ ፡ ወይም ፡ ሞግዚቱ ፡
ወይም ፡ ሌሎች ፡ (ዘመዶቹ) ፡ ገና ፡ ትንሽ ፡ ሳለ፡
መልካም ፡ ደም ፡ ግባት ፡ ካላት ፡ ዘንድ ፡
ወይም ፡ ስለገንዘቧ ፡ ብዛት ፡ ወይም ፡ ስለዘመ
ዶቿ ፡ ክብር ፡ ወይም ፡ ስለጌጧ ፡ ወይም ፡ ስለ
ልብሶቿ ፡ እንዳታመልጠው ፡ ወድዶ ፡ ሲላ
ውን ፡ ስለመቅደም ፡የሚያጋባው ፡ አለ ። ያም ፡
ባይሆን ፡ ከፈቃዳት ፡ (ከፍላጎት) ፡ ከፋት ፡ የተ
ነሣ ፡ ፈርቶ ፡ ለመጠበቅ ፡ ለጥፋት ፡ ስለምታደ
ርስ ፡ ስለፍትወት ፡ መታወክ ፡ አስቀድሞ ፡ የሚ
ያጋባው ፡ አለ ። ወይም ፡ ስለምትሄድ ፡ እናቱ ፡
መታወክ ፡ (ማዘን) ፡ ለአንዲት ፡ ሰዓት ፡ በእርስ
ደስ ፡ ይላት ፡ ዘንድ ፡ ከሞት ፡ አስቀድሞ ፡ ወይ
ም ፡ ከችግር ፡ አስቀድሞ ፡ የዚህን ፡ ጥቅም ፡
ሽተው ፡ ወይም ፡ ስለማሳዘንና ፡ ስለመከራከር ፡
ወይም ፡ ስለመብት ፡ የሚያጋቡ ፡ አሉ ። ከእነር
ሱም ፡ ወገን ፡ በመልካም ፡ አሳቡ ፡ ልጅን ፡ የሚሻ
አለ ። ይኸውም ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ቢኖረው ፡
የሚወርሰው ፡ ልጅ ፡ ሽቶ ፡ ነው ። ከነዚህ ፡

ባቲ ፡ ወዘኢተሰዋ ፡ ላቲ ፡ ወብዙኃን ፡ የኀብኡ ፡ ጣዕመ ፡ ፍትወት ፡ ዘፈቀዶሙ ፡ በዘይትኀሠሥ ፡ እምኀሠሣዘሮሙ ፡ ለተራድኦ ፡ ዘሲሲት ።

፰፻፵ ወናሁ ፡ ረከበ ፡ ፩ዱ ፡ ጠቢብ ፡ ፍካሬ ፡ ዝንቱ ፡ በብሂሎቱ ፡ እስመ ፡ ፍትወት ፡ ይእቲ ፡ እሞን ፡ ለኀሣሬት ፡ ወስድካማት ፡ ወጸማት ፡ ወኀሣር ፡ ወበእማን ፡ ወላዲት ፡ ሕማም ፡ ይእቲ ፡ ለሥጋውያን ፡ ወለነፍሳውያን ፡ እስመ ፡ ይእቲ ፡ ታተልዎን ፡ ለመፍትዳት ፡ ብዙኃት ፡ እለ ፡ ኢይትፈቀዳ ፡ ወትሬስዮን ፡ ከመ ፡ ዘይትፈቀዳ ። ወንስአሎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተሰናእዎ ፡ ወረድ ድኤተ ፡ ውኀይለ ፡ ወምሕረተ ፡ አሜን ።

፰፻፵፩ ምዕራፍ ፡ ዳግማዊት ። በእንተ ፡ ሕዒ ፡ ወው እቱ ፡ ፬ቱ ፡ ዖታ ። ቀዳማዊ ፡ እስመ ፡ ሕዒ ፡ ኢይሤኒ ፡ ለዘኢተጠየቀ ፡ አውሰቦቱ ። ወዳግ ምኒ ፡ ዘየሐዕዩ ፡ ሎቱ ፡ ለእመ ፡ ኢኮነ ፡ ጥዩቀ ፡ ታሕተ ፡ ምልክና ፡ ካልኡ ፡ ይከውኖ ፡ ከመ ፡ ይሕዒ ፡ ለርእሱ ፡ እመአኮ ፡ በርእሱ ፡ አው ፡ በመጽሐፈ ፡ መልእክቱ ፡ አው ፡ በዘይሠምሮ ፡ ለከዊነ ፡ ሀረቲ ። ወተከሥቶቱ ፡ ሕዒሰ ፡ መባ ሕት ፡ ሎቱ ፡ ለርእሱ ፡ አው ፡ በመጽሐፉ ፡ አው ፡ በዘይፈቅዶ ፡ ለከዊነ ፡ ሀረቲ ። ማልሳ ዊኒ ፡ ናቀድም ፡ ዝክረ ፡ ተዋስቦ ፡ ዘሕጉም ፡ እምኔሁ ፡ ከመ ፡ ኢይግበሩ ፡ ቦቱ ፡ ሕዒ ፡ ወና ኀረተ ። ወውእቱኒ ፡ ይትከፈል ፡ ኀበ ፡ ፲ወ፰ቱ ፡ አክፋል ።

፰፻፵፪ ክፍል ፡ ቀዳማዊ ፡ አውስቦ ፡ አዝማድ ፡ ዘበ ሥጋ ፡ ወለእመኒ ፡ ኢኮነ ፡ እምነ ፡ ተዋስቦ ፡ ሕጋዊ ። ጠሰ ፡ ፮ቱ ፡ ወእሉ ፡ እሙንቱ ፡ ኀበ ፡ ፫ቱ ፡ ዖታ ፡ እለ ፡ ዘመልዕልት ፡ ወውእቶሙ ፡ ወላድያን ፡ ወእምሒዋን ፡ ወዘይትሌሀሉ ፡ ወዘይቴሐቲ ፡ ወውእቶሙ ፡ ውሉድ ፡ ወውሉ ዶሙ ፡ ወዘይወርዱ ። ወእለ ፡ እምኀበዋት ፡ ወው እቶሙ ፡ አኃው ፡ አበው ፡ ወአኃት ፡ አበው ፡ አኃው ፡ እማት ፡ ወአኃት ፡ እማት ፡ ወአኃው ፡ ወውሉደ ፡ አኃው ። ወእሉ ፡ ካዕበ ፡ እለ ፡ ይዘ



ከተነገሩ ፡ ክፍሎች ፡ የደስታ ፡ ክፍል ፡ ያልሆነ ፡ ልዩ ፡ ፈቃድን ፡ ለማግኘት ፡ አንችልም ። በእ ርሷ ፡ አንድ ፡ ያልሆነ ፡ እርሷን ፡ ያልተከተለ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ልናገኝ ፡ አንችልም ። ብዙዎቹ ፡ ክፍላጎታቸው ፡ የተነሣ ፡ በሚገልጡ ፡ ገንዘብ ፡ የሚወዱትን ፡ የፍትወት ፡ ጣዕም ፡ በምግብ ፡ ለመረዳዳት ፡ ይሸሽጋሉ ።

፰፻፵ እነሆ ፡ አንድ ፡ ፈላስፋ ፡ ፍትወት ፡ ለኀሣር ፡ ለድካም ፡ ለፃማ ፡ ለተዋርዶ ፡ እናታቸው ፡ (መገ ኛቸው) ፡ ናት ፡ በማለቱ ፡ የዚህን ፡ ትርጓሜ ፡ አገኘ ፡ (ተናገረ) ። በእውነትም ፡ ለሥጋውያ ንና ፡ ለመንፈሳውያን ፡ የመከራ ፡ መገኛ ፡ ናት ። የማይወደዱትን ፡ ብዙዎችን ፡ ፈቃዶች ፡ ታስ ከትላቸዋለችና ። እንደሚወደዱም ፡ ታደርጋቸ ዋለችና ። መሰማማትን ፡ ርዳታን ፡ ኀይልን ፡ ይቅርታን ፡ ይሰጠን ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንለምነው ፡ አሜን ።

፰፻፵፩ ሁለተኛው ፡ ምዕራፍ ፡ ስለመተጫጨት ፡ ይና ገራል ። ይኸውም ፡ አራት ፡ ወገን ፡ ነው ። መጀ መሪያው ፡ ማግባቱ ፡ ላልተረጋገጠ ፡ ሰው ፡ ማጨት ፡ አይገባምና ። ሁለተኛውም ፡ የሚያ ጭጭለት ፡ ሰው ፡ በሌላው ፡ ሞግዚትነት ፡ ስር ፡ በእርግጥ ፡ ካልሆነ ፡ ለራሱ ፡ ሊያሳጭ ፡ ያም ፡ ባይሆን ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፎ ፡ ወይም ፡ ሽማግሌ ፡ ሊሆነው ፡ በሚወደው ፡ ሊያጭ ፡ ይገባዋል ።

ማጫውን ፡ ግን ፡ ራሱ ፡ ወይም ፡ በደብዳቤው ፡ ወይም ፡ ሽማግሌ ፡ ሊሆነው ፡ በሚወደው ፡ ሰው ፡ ለመግለጥ ፡ (ለመስጠት) ፡ መብት ፡ አለው ። ፫ኛውም ፡ መተጫጨት ፡ ማጫ ፡ መሰ ብት ፡ እንዳይደረግበት ፡ ከርሱ ፡ የተከለከለ ውን ፡ ጋብቻ ፡ መናገርን ፡ እናስቀድማለን ። ይኸውም ፡ ከ፲፰ ፡ ወገን ፡ ይከፈላል ።

፰፻፵፪ መጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ የሥጋ ፡ ዘመዶች ፡ ጋብቻ ፡ ነው ። ከሕግ ፡ ጋብቻም ፡ ወገን ፡ ባይ ሆን ። ጠስ ፡ ፮ ። እሊህም ፡ ፫ ፡ ወገን ፡ ናቸው ። ወደላይ ፡ ያሉ ፡ ወላጆች ፡ አያቶች ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያሉ ፡ ቅድመ ፡ አያቶች ፡ ናቸው ። ወደ ታች ፡ ያሉትም ፡ ልጆች ፡ የልጅ ፡ ልጆች ፡ የልጅ ፡ ልጆች ፡ ልጆች ፡ ናቸው ። ወደጐን ፡ ያሉትም ፡ የባቶች ፡ ወንድሞች ፡ ያባቶች ፡ እኅ ቶች ፡ የእናት ፡ ወንድሞችና ፡ እኅቶች ። ወንድ ሞች ፡ የወንድሞች ፡ ልጆች ፡ ዳግመኛም ፡ ከእ

መዱ ፡ ወይሰናስሉ ፡ እስመ ፡ ተወልዱ ፡ እምአበው ፡ ወእምሔዋን ።

፳፻፶፫ ወክርስቲያንስ ፡ በዝንቱ ፡ ግብር ፡ ኅበ ፡ ፪ቱ ፡ ምክራት ፡ ቀዳማዊሰ ፡ ተከልአ ፡ በ፫ቱ ፡ ትውልዳት ፡ ወብውሕት ፡ ራብዒት ፡ ወዘድኅሬሃ ፡ ወእለ ፡ ከመዝ ፡ ይገብሩ ፡ እሙንቱ ፡ ግብጻውያን ፡ ወንስጥሮሳውያን ፡ ወመንፈቆሙ ፡ ለሰብአ ፡ ሶርያ ። ወተገበሩ ፡ ዘከመ ፡ ቀኖና ፡ ሐዋርያት ፡ በበይነ ፡ ዘኢያንበረት ፡ ውእተ ፡ ወቀኖና ፡ ጉባዔ ፡ ዘኒቅያ ፡ ዘየኀብር ፡ ላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ ወፈድፋደስ ፡ ቀኖና ፡ ነገሥት ፡ በእንተ ፡ ዘኢትክልእ ፡ ተዋስቦ ፡ እምትውልድ ፡ ራብዕ ፡ ፍጹመ ፡ ወኢትክልእ ። ወኀለፈ ፡ ዝንቱ ፡ ሥርዓት ፡ ኀበ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ከመ ይፍትሑ ፡ ኪያሁ ፡ ወይእስሩ ፡ በፍትሕ ፡ ዘይሤኒ ፡ ለበቍዔት ፡ ወበዘኢይትቃረን ፡ ሕገ ። ወናሁ ፡ ተጠየቀ ፡ በአንቀጽ ፡ ደኃራዊ ፡ ከመ ፡ ዝንቱ ፡ ድልው ፡ ሎሙ ። ወሶበ ፡ ርእዩ ፡ ከመ ፡ ውእቶሙ ፡ ኮኑ ፡ ምሉካነ ፡ ወሕጹጻነ ፡ እምነ ፡ ጐልቆሙ ፡ ብዙኅ ፡ በውስተ ፡ ሀገሮሙ ፡ እስከ ፡ ኢይትረከቡ ፡ ወራዙት ፡ ወውርዝዋት ፡ እምትውልድ ፡ ሳብዕ ። ወአልቦ ፡ እምድኅሬሃ ፡ ዘትከውን ፡ ምስሌሃ ፡ አውስቦ ፡ ወተፈጸመ ፡ ዝንቱ ፡ ሳዕለ ፡ አማስኖ ፡ ንጽሖሙ ፡ ለተመዋዕያን ፡ እምፍትወት ፡ ወእመቦ ፡ ዘተዐደወ ፡ ለወፂእ ፡ እምሃይማኖቶሙ ፡ በምክንያተ ፡ ዝንቱ ። ርእዩ ፡ ከመ ፡ ሠናይ ፡ ዝንቱ ፡ ወብዉሕ ፡ አውስቦ ፡ እምትውልድ ፡ ራብዕ ።

፳፻፶፬ ወምክር ፡ ካልእት ፡ ተከልአ ፡ እም፮ቱ ፡ ትውልዳት ፡ ወድልው ፡ ሳብዓይ ። ወካልአን ፡ ከልኡ ፡ አውሰቦ ፡ ልደት ፡ ሳድሲት ፡ ወአብሑ ፡ አውስቦ ፡ ልደት ፡ ሳብዒት ፡ ወውእቶሙ ፡ መለካውያን ፡ ወተገበሩ ፡ በከመ ፡ አንበሮ ፡ ራብዕ ፡ አብጥሊስ ፡ ዘ፮ቱ ። ወውእቱ ፡ በብሂሎቶሙ ፡ እመሰ ፡ ኮነ ፡ መዓርግ ፡ ራብዕ ፡ ወእምነ ፡ ዝንቱስ ፡ መዓርግ ፡ ኢያዖሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ አውስቦ ፡ ወኢብዉሕ ፡ አውስቦተ ፡ ደቂቀ ፡ አኃወ ፡ አብ ፡ በከመ ፡ ተነግረ ፡ ቅድመ ፡ በቀኖና ፡ ጉባኤሆሙ ፡ ዘባሕቲቶሙ ፡ ዘንቡር ፡ ምስሌሆሙ ።

፳፻፶፭ ወሶበ ፡ ርእዩ ፡ ካልአኒሆሙ ፡ ዘኮነ ፡ ቦሙ ፡



ባቶችና ፡ ከአያቶች ፡ ስለተወለዱ ፡ የተያያዙ ፡ ዘመዶች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

፳፻፶፫ "ክርስቲያን ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ሥራ ፡ ወደሁለት ፡ አስተያየት ፡ ናቸው ። መጀመሪያው ፡ በ፫ኛ ፡ ትውልድ ፡ መከልከል ፡ ነው ። አራተኛዋ ፡ የተፈቀደች ፡ ናት ። ከእርሷም ፡ በኋላ ፡ ያለው ፡ እንደዚህ ፡ የሚያደርጉ ፡ ግብፃውያን ፡ ንስጥሮሳውያን ፡ ከሦርያ ፡ ሰዎች ፡ እኩሌቶቹ ፡ ናቸው ። የሐዋርያት ፡ መጽሐፍ ፡ ይህን ፡ ስላልጻፈች ፡ እንደዚያው ፡ አደረጉ ። የኒቅያ ፡ የጉባኤ ፡ ሕግም በዚህ ፡ የሚስማማ ፡ ነው ። ይልቁንም ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ከ፬ኛው ፡ ትውልድ ፡ ጀምሮ ፡ መጋባትን ፡ ፈጽሞ ፡ ስለማትከለክል ። ለጥቅም ፡ በሚበጅ ፡ ፍርድ ፤ ሕግንም ፡ በማይቃወም ፡ ገንዘብ ፡ እርሱን ፡ ይፈቱ ፡ ያሥሩ ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ሥራት ፡ ወደሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ተላለፈ ። ይህም ፡ ለእነርሱ ፡ የሚገባቸው ፡ መሆኑ ፡ በኋለኛው ፡ አንቀጽ ፡ እነሆ ፡ ተረጋግጧል ። እነርሱ ፡ ተገኘች፡ እንደሆኑ ፡ ከ፯ኛው ፡ ትውልድ ፡ በኋላ ፡ ጎበዛዝትና ፡ ቆነጃጅት ፡ እስከማይገኙ ፡ ድረስ ፡ በሀገራቸውም ፡ ውስጥ ፡ ከብዙ ፡ ቍጥራቸው ፡ እንዳነሱ ፡ ከእርሷም ፡ በኋላ ፡ ከእርሷ ፡ ጋራ ፡ ጋብቻ ፡ የምትሆን ፡ ትውልድ ፡ እንደሌለች ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ከፈቲው ፡ የተነሣ ፡ ንጽሕናቸውን ፡ በማሳደፍ ፡ ድል ፡ ለሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ይህ ፡ ተፈቀደ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ከሃይማኖታቸው ፡ ለመውጣት ፡ የተደፋፈረ ፡ ቢኖር ፡ ይህ ፡ መልካም ፡ እንደሆነ ፡ ተመለከቱ ፡ ከአራቱ ፡ ትውልድ ፡ አንሥቶ ፡ መጋባት ፡ የተፈቀደ ፡ ነው ።

፳፻፶፬ ሁለተኛው ፡ አስተያየት ፡ ከ፮ኛው ፡ ትውልድ ፡ መከልከል ፡ ነው ። ሰባተኛው ፡ ትውልድ ፡ ግን ፡ የተፈቀደ ፡ ነው ። ሌሎች ፡ ደግሞ ፡ የስድስተኛውን ፡ ትውልድ ፡ ግቢ ፡ ከልክለው ፡ የሰባተኛይቱን ፡ ትውልድ ፡ ፈቀዱ ። እኒኸውም ፡ መለካውያን ፡ ናቸው ። አራተኛው ፡ አብጥሊስ ፡ በ፮ኛው ፡ እንደጻፈው ፡ አደረጉ ። ይኸውም ፡ አራተኛ ፡ ትውልድ ፡ ከሆነ ፡ ከዚህ ፡ ትውልድ ፡ ጋብቻ ፡ ሊሆን ፡ አይገባም ። የአባትን ፡ የወንድም ፡ ልጅ ፡ ማግባት ፡ አይገባም ፡ በማለታቸው ነው ። ከእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ባለ ፡ ለብቻቸው ፡ በሚሆን ፡ በጉባኤያቸው ፡ መጽሐፍ ፡ አስቀድሞ ፡ እንደተነገረ ።

፳፻፶፭ ሌሎችም ፡ አስቀድሞ ፡ ከተነገረው ፡ ርኵሰት ፡

እምነ ፡ ርኅሰ ፡ ዘቀደመ ፡ ሀከሮቱ ፡ ነገርዎሙ ፡ ለሊቃውንተ፡ሆሙ ፡ ዘሀለወ ፡ ውስተ ፡ ሀገረ ፡ ትእዛዞሙ ፡ ወአብሕዎሙ ፡ ሳድሲተ ። ወጸንዑ ፡ ላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ እስከ ፡ ይእዜ ፡ ወኢረብሞሙ ፡ ምንተኒ ፡ ወቦአ ፡ ውስተ ፡ ሕርትምና ፡ እስከ ፡ ይትዋሰብ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ በእንተ፡ ውእቱ ፡ እምዘ ፡ ኢኮነ ፡ ዘይሰነአዎሙ ።

ወገን ፡ የሆነባቸውን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ በሚያዝዙበት ፡ ሀገር ፡ ላሉ ፡ አለቆቻቸው ፡ ነገሯቸውና ፡ ስድስተኛዋን ፡ ፈቀዱላቸው ። እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ በዚሀ ፡ ላይ ፡ ጸኑ ። ወደጥፋት ፡ ገቡ ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ አልጠቀማቸውም ። ስለዚሀ ፡ ነገር ፡ ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ የሚስማማው ፡ ካልሆነ ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ እስኪጋባ ፡ ድረስ ።

፰፻፶፮ ወጕልቈ ፡ ትውልዳትሰ ፡ ዘይከውን ፡ በአውስቦ ፡ ወለተ ፡ እኁወ ፡ አብ ፡ ራብዓት ፡ ይእቲ ፡ በአምሳል ፡ በከመ ፡ ይብል ፡ አቡየ ፡ ወለደኒ ፡ ወእምኔውየ ፡ ወለዶ ፡ ለእቡየ ። ወእሉ ፡ ፪ቱ ፡ ትውልዳት ፡ እሙንቱ ፡ ወእምኔውየ ፡ ወለዶ ፡ ለእኁወ ፡ አቡየ ፡ ወእኁወ ፡ አቡየ ፡ ወለዳ ፡ ለወለቱ ፡ ወእሉ ፡ ትውልድ ፡ አርባዕቱ ።

፰፻፶፮ በጋብቻ ፡ የሚሆን ፡ የትውልድ ፡ አቆጣጠር ፡ ግን ፡ የአባት ፡ የወንድም ፡ ልጅ ፡ አራተኛ ፡ ናት ። ለምሳሌ ፡ አባቴ ፡ እኔን ፡ ወለደኝ ፡ አያቴም ፡ አባቴን ፡ ወለደው ። እሊህ ፡ ሁለት ፡ ትውልድ ፡ ናቸው ። አያቴም ፡ የአባቴን ፡ ወንድም ፡ ወለደው ። የአባቴ ፡ ወንድምም ፡ ልጁን፡ ወለዳት ። እሊህ ፡ አራት ፡ ትውልድ ፡ ናቸው ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፰፻፶፯ ክፍል ፡ ዳግማዊ ፡ እውስቦ ፡ እዝማድ ፡ እመንገለ ፡ ሕግ ። ወእሙንቱ ፡ ተሐባይያን ፡ ውሉደ፡ ካልእኒሆሙ ፡ በጥምቀተ ፡ ክርስትና ። ዘኒቅየ ፡ ፰ወ፫ቱ ፡ ፰ወ፭ቱ ፡ ጠስ ፡ ፯ቱ ፡ መጅ ፡ ፭ቱ ፡ ዘተሐበይዎ ፡ ወዘሂተሐበየ ፡ ኢይትዋሰብ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ምስለ ፡ ካልኡ ፡ ወኢወሳድያኒሁ ።

፰፻፶፯ ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ከሕግ ፡ ወገን ፡ የዘመድን ፡ ጋብቻ ፡ ይናገራል ። እሊህም ፡ የሌሎችን ፡ ልጆች ፡ በጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ የተናሱ ፡ ናቸው ኒቅያ ፡ ፰፫ ፡ ፰፭ ። ጠስ ፡ ፯ ። መጅ ፡ ፭ ። ክርስትና ፡ እንሽውና ፡ ተነሹ ፡ አንዱ ፡ ከሁለተኛው ጋራ ፡ አይጋቡ ። ወላጆቹም ።

፰፻፶፰ ወውስተ ፡ ቀኖና ፡ ዘነገሥት ፡ ወኢአኃዊሁ ፡ ወኢውሉዱ ፡ ወኢውሉደ ፡ ውሉዱ ፡ ወኢውሉደ ፡ ብእሲቱ ፡ ወኢውሉደ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ፡ ለውሉደ ፡ ካልኡ ። ወኢታስተዋስብ ፡ ብእሲት ፡ ወለታ ፡ ለብእሲ ፡ ዘተሐበዮ ፡ ምታ ፡ በጥምቀተ ክርስትና ፡ ወከማሁ ፡ ብእሲኒ ፡ ኢያስተዋስብ ፡ ወለቶ ፡ ለብእሲ ፡ ዘተሐበየቶ ፡ ብእሲቱ ። ወለእሉ ፡ ኵሎሙ ፡ ኮነ ፡ ማእከሌሆሙ ፡ ተዘምዶ ፡ መንፈሳዊ ፡ ወዘገብረ ፡ ዘንተ ፡ ይኩን ፡ እምሳለ ፡ መምለኬ ፡ ጣዖት ፡ ወመጸብሐዊ ፡ እስከ ፡ ይትፈለጥ ፡ ወያኔስሕ ፡ እምነ ፡ ኃጢአቱ ። ወለእኢዘኩራንስ ፡ ብዉሕ ፡ ሎሙ ፡ ከመ ፡ ያውስቡ ።

፰፻፶፰ በፍትሐ ፡ ነገሥትም ፡ ወንድሞቹም ፡ ልጆቹም ፡ የልጅ ፡ ልጆቹም ፡ የሚስቱ ፡ ልጆች ፡ ከሌላው ፡ ልጆችም ፡ ወገን ፡ ያንዱ ፡ ልጆች ፡ ከሁለተኛው፡ ልጅ ፡ ጋራ ፡ አይጋቡ ። ሴት ፡ ልጅዋን ፡ ባሏ ፡ ክርስትና ፡ ላነሣው ፡ ወንድ ፡ አታጋባ ። ወንድም ፡ እንደዚሁ ፡ ልጁን ፡ ሚስቱ ፡ ክርስትና ፡ ላነሣቸው ፡ ወንድ ፡ አያጋባ ። በእነዚሀ ፡ ሁሉ ፡ በመካከላቸው ፡ መንፈሳዊ ፡ ተዘምዶ ፡ ሆኗል ፡ (እለ) ፡ ይህን ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፡ እንደ መምለኬ ፡ ጣዖት ፡ እንደ ፡ መጸብሐዊ ፡ (ቀራጭ) ፡ ይሁን ። ከኃጢአቱ ፡ እስኪመለስና ፡ እስኪለይ ፡ ድረስ ። ላልተነገሩት ፡ ግን ፡ መጋባት ፡ ይገባቸዋል ።

፰፻፶፱ ወናሁ ፡ ተነግረ ፡ በእንተ ፡ ተዋስቦ ፡ ተሐባይያን ፡ በጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ ቃል ፡ ዘኢይሰነአው ፡ ቦቱ ፡ ወዘኢይትገበሩ ፡ ኪያሁ ። ተብህለ ፡ ኢይኩን ፡ ማእከሌሆሙ ፡ ተዋስቦ ፡ ወከማሁ ፡ ውሉዶሙ ፡ ወእልቦሙ ፡ ሥርዓት ፡ ለዘቱ ፡ ኃጢአት ፡ መንፈሳዊት ፡ ዘእንበለ ፡ በተፈልጦ ፡ ወንስሐ ። ወያደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ንስሐሆሙ ፡ በምንኵስና ፡ እመ ፡ ፈቀዱ ፡ መድኀኒተ ፡ ነፍሱ ።

፰፻፶፱ በጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ ስለተነሳሱ ፡ ሰዎች ፡ ጋብቻ ፡ የማይስማሙበት ፡ ርሱን ፡ የማያደርጉት ነገር ፡ እነሆ ፡ ተነገረ ። በመካከላቸው ፡ መጋባት ፡ አይሁን ፡ ተባለ ። ልጆቻቸውም ፡ እንደዚሁ ። በመለየት ፡ በንስሐ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በዚች ፡ መንፈሳዊት ፡ ኃጢአት ፡ ሥርዓት ፡ የላቸውም ። ድኅነተ ፡ ነፍሱን ፡ ከወደደ ፡ ንስሐቸው ፡ በምንኵስና ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ።

አንቀጽ ፡ ፳፬ ።

፳፻፶ ክፍል ፡ ሣልስ ፡ እውስቦ ፡ አዝማድ ፡ በንብ
ረት ፡ ወለእመኒ ፡ ወፅኡ ፡ እምታሕተ ፡ ምልክ
ናሆሙ ፡ ውእቶሙ ፡ ወእመ ፡ ተፈልጡ ፡ ዘሐበ
ንዎሙ ፡ ወእሙንቱ ፡ ዘሀለዉ ፡ በተሳትፎ ፡
ጠቢወ ፡ ጥብ ፡ አው ፡ በእልህቆ ፡ በመዓርገ ፡
ውሉድ ፡ ወውሉዶሙ ፡ ወወላድያኒሆሙ ፡
ወለእመኒ ፡ እሉ ፡ ወአበዊሆሙ ፡ ወአበወ ፡ አበ
ዊሆሙ ፡ ወአኀወ ፡ አበዊሆሙ ፡ ወአኀወ ፡ እማ
ቲሆሙ ፡ ወአኃተ ፡ እማቲሆሙ ፡ ወብእሲተ ፡
አብ ። ወኢያውስብ ፡ አብ ፡ ብእሲተ ፡ ዘትከ
ውኖ ፡ ወለተ ፡ ወትትሐፀን ፡ ቦቱ ። ወከዊኖ ፡
አብናስ ፡ ከመዝ ፡ ውእቱ ፡ አምሳለ ፡ እምኔውየ
ሐፀነ ፡ ወለተ ፡ ወከነ ፡ አቡየ ፡ ይሰምያ ፡ እኅቶ፡
ወይእቲ ፡ እኅተ ፡ አቡየ ፡ በምዕቅብና ፡ አው ፡
እምየ ፡ አጥበወት ፡ ወለተ ፡ ወአልሀቀታ ፡ ምስ
ሌየ ፡ ወይእቲኒ ፡ እኅትየ ፡ በንብረት ። ወዝን
ቱኒ ፡ ሀሰወ ፡ በቀኖና ፡ ነገሥት ።

፳፻፶፩ ወመጽሐፈ ፡ ድስቅስ ፡ ትኤዝዞ ፡ ለስብእ ፡
በ፲ወ፰ቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ከመ ፡ ያስተዋስብ ፡
ብእሲ ፡ ለወልዱ ፡ እንለ ፡ ማውታ ፡ ዘሐፀኖ ፡
ወዝንቱስ ፡ ይከውኖ ፡ ሎቱ ፡ ገቢረ ፡ ትሕትና ፡
ወምሕረት ፡ ወውእቱ ፡ ዘይደሉ ፡ ወዘይኄይስ ።

፳፻፶፪ ሥርዋጽ ፡ ነበረ ፡ ውስተ ፡ ቀኖና ፡ ነገሥት ።

፳፻፶፫ ክፍል ፡ ራብዕ ፡ በእንተ ፡ አውስቦ ፡ አዝማድ ፡
እመንገለ ፡ ተዋስቦ ፡ ወእሉ ፡ እምከዊነ ፡ ትው
ልድ ፡ ወእማንቱ ፡ አንስትያ ፡ አበው ፡ ወእምኔ
ዎን ፡ ወአኀቲሆን ፡ ወእማቲሆን ፡ ወእምኔው
ቶን ። ወአንስትያ ፡ ውሉድ ፡ ወደቂቆሙ ፡ ወአ
ኃቲሆን ፡ ወእማቲሆን ፡ ወእምኄውቶን ። ወአ
ንስትያ ፡ አኀው ፡ ወደቂቆሙ ፡ ወአኃቲሆን ፡
ወእማቲሆን ፡ ወእምኄውቶን ፡ ወአዝማደ ፡
ብእሲት ፡ ዘውእቶን ፡ እምኄውታ ፡ ወእማ ፡
ወእኅተ ፡ አቡሃ ፡ ወእኅተ ፡ እማ ፡ ወእኅታ ፡
ወወለታ ፡ ወወለተ ፡ ወልዳ ። ወአንስትያ ፡
አዝማዲሃ ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡ ውስተ ፡ ዛቲ ፡ መዓ
ርግ ፡ ወኵሉ ፡ ዘአሕረሙ ፡ ሳዕለ ፡ ብእሲቱ ፡
ከማሁ ፡ ሕሩም ፡ ውእቱ ፡ ላዕለ ፡ ምታኒ ።

፳፻፶፬ ክፍል ፡ ኃምስ ፡ ተዋስቦተ ፡ ዘአማኅፀንዎ ፡
ምስለ ፡ እንተ ፡ አመኀብዎ ፡ ሳዕለ ፡ አስተዋስ
ቦታ ። ወእዙዝ ፡ ውእቱ ፡ ወደቂቁ ፡ ወአኀዊሁ ፡

ስለ ፡ ጋብቻ ።

፳፻፶ ፫ኛው ፡ ክፍል ፡ አብሮ ፡ በመኖር ፡ የተዛመዱ ፡
ሰዎችን ፡ ጋብቻ ፡ ይናገራል ። ምንም ፡ እነርሱ ፡
ከሞግዚትነት ፡ ስር ፡ ቢወጡ ፡ አሳዳጊዎቻ
ቸውም ፡ ቢለያዩ ። እኒህም ፡ ጡት ፡ መጥባትን፡
በመስተፍ ፡ ወይም ፡ በልጆች ፡ መዓርግ ፡ በማ
ሳደግ ፡ ያሉ ፡ ናቸው ። ልጆቻቸውም ፡ ወላጆቻ
ቸውም ፡ እነርሱም ፡ ቢሆኑ ፡ አባቶቻቸውም ፡
ያባቶቻቸው ፡ አባቶችም ፡ ያባቶቻቸው ፡ ወንድ
ሞች ፡ የእናቶቻቸው ፡ ወንድሞች ፡ የእናቶቻ
ቸው ፡ እቶች ፡ ያባት ፡ ሚስት ፡ (የእንጀራ ፡
እናት) ፡ አባት ፡ ልጅ ፡ ትሆነኛለች ፡ ብሎ ፡ ያሳ
ደጋትን ፡ ሴት ፡ አያግባ ። የአባትነትም ፡ አኳኋ
ን ፡ እንደዚህ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ አያቴ ፡ ሴት ፡
ልጅ ፡ አሳደገ ። አባቴም ፡ እኅቴ ፡ ይላታል ።
ይህችም ፡ አብሮ ፡ በማደግ ፡ የአባቴ ፡ እኅት ፡
ናት ። ወይም ፡ እናቴ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ጡት ፡ እያ
ጠባች ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ አሳደገች ። ይህችም ፡
አብሮ ፡ በማደግ ፡ እህቴ ፡ ናት ። ይህም ፡ በፍ
ትሐ ፡ ነገሥት ፡ አለ ።

፳፻፶፩ መጽሐፈ ፡ ዲድስቅልያ ፡ ግን ፡ በ፲፰ኛው ፡ ትእ
ዛዝ ፡ ላሳደገው ፡ ድኃ ፡ አደግ ፡ ልጁ ፡ እንዲያጋ
ባው ፡ ሰውን ፡ ታዝዘዋለች ። ይኸውም ፡ ትሕ
ትና ፡ ምሕረት ፡ እንደማድረግ ፡ ይሆንለታል ።
ይኸውም ፡ የሚገባ ፡ የተሻለ ፡ ነው ።

፳፻፶፪ ሰርዋጽ ። በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ተጽፎአል ።

፳፻፶፫ ፬ኛ ፡ ክፍል ። በትውልድ ፡ ያይደለ ፡ በግቢ ፡
ስለሚዛመዱ ፡ ሰዎች ፡ መጋባት ፡ ይናገራል ።
እኒህም ፡ ያባቶች ፡ ሚስቶች ፡ ወንድ ፡ አያቶቻ
ቸው ፡ እኅቶቻቸው ፡ እናቶቻቸው ፡ ሴት ፡
አያቶቻቸው ። የልጆች ፡ ሚስቶች ፡ ልጆ
ቻቸውም ፡ እኅቶቻቸውም ፡ እናቶቻቸውም ፡
ሴት ፡ አያቶቻቸውም ። የወንድሞች ፡ ሚስቶች ፡
ልጆቻቸው ፡ እኅቶቻቸውም ፡ እናቶቻቸው ፡
ሴቶች ፡ አያቶቻቸው ፡ ናቸው ። የሴት ፡ ዘመ
ዶችም ፡ እነርሱም ፡ አያቷ ፡ እናቷ ፡ ያባቷ ፡
እኅት ፡ የእናቷ ፡ እኅት ፡ እኅቷ ፡ ልጅዋ ፡
የልጅ ፡ ልጅዋ ፡ ናቸው ። በዚች ፡ ትውልድ ፡
ያሉ ፡ የዘመዶቿ ፡ ሚስቶች ፡ በሴቲቱ ፡ ላይ ፡
የከለከሉት ፡ ሁሉ ፡ እንዲሁም ፡ በባሏ ፡ በኩል ፡
የተከለከለ ፡ ነው ።

፳፻፶፬ አምስተኛ ፡ ክፍል ። ሊያጋባት ፡ ከሾሙት ፡
ጋር ፡ አደራ ፡ ያስጠበቁትን ፡ ሰው ፡ ጋብቻ ፡
ይናገራል ። ይኸውም ፡ እርሱ ፡ ልጁ ፡ ወንድ

ምስለ ፡ ዙሉ ፡ ንዋይ ፡ ዘእንበለ ፡ እምድኅረ ፡ ኮነ ፡ ላቲ ፡ ፳ወ፫ቱ ፡ ዓመት ። ወእምድኅረ ፡ ፈጸመ ፡ ዘአማኅፀንዎ ፡ ዘይደሉ ፡ ላዕሌሁ ፡ እምነ ፡ ሐሳብ ።

፳፻፶፭ ክፍል ፡ ሳድስ ፡ ወእኮ ፡ ሠናይ ፡ ከመ ትትወሰብ፡ ብእሲት ፡ መላኪ ፡ ለገብር ፡ ዘአግዓዞ ፡ ምታ ።

፳፻፶፮ ክፍል ፡ ሳብዕ ፡ እውሰቦ ፡ ምእመን ፡ ለዘኢኮነት ፡ እማኒተ ፡ እንተ ፡ ኢኮነት ፡ ክፍለ ፡ ዚአሁ ፡ ከመ ፡ ዘይወስክ ፡ ላዕለ ፡ ገቢረ ፡ ትሩፋቲሁ ።

፳፻፶፯ ክፍል ፡ ሳምን ፡ ዘይከልእ ፡ እምተራክቦ ፡ ዘይትፈቀድ ፡ ለተዋስቦ ፡ ወውእቱ ፡ ዝንቱ ፡ እመኒ ፡ ፍጥረታዊ ፡ ዘከመ ፡ ሕጸው ፡ እምከርሠ ፡ እሙ ፡ ወውእቱ ፡ ዘኢይትከሀሎ ፡ በፍጥረቱ ፡ ተደምሮ ፡ ዘዘከርነ ። ወፈናፍንታም ፡ ውእቱኒ፡ ዘቦቱ ፡ ኅፍረተ ፡ ተባዕት ፡ ወአንስት ፡ ኅቡረ ፡ በ፩ዱ ፡ መካን ። ወብእሲትኒ ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ዓፅም ፡ ውስተ ፡ ዘይከልእ ።

፳፻፶፰ ወዘተዳድቀሰ ፡ ፪ቱ ፡ ዖታ ፡ እሙንቱ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ሕጸው ፡ ወካልኡ ፡ ዐብድ ፡ ዘይከውን ፡ ሕጹጸ ፡ በልቡናሁ ። ወዛልለ ፡ ደዊያት፡ መታርያን ፡ ዘከመ ፡ ዝልጋሴ ፡ ወበእንተ ፡ ለምጽለ ፡ ይኩን ፡ በከመ ፡ ኅረየ ፡ ለሊሁ ። ወናሁ ፡ ዘከርነ ፡ ሥርዓተ ፡ ዝንቱ ፡ ክፍል ፡ በውስተ ፡ ምዕራፍ ፡ ዘያፀርዕ ፡ ተዋስቦ ።

፳፻፶፱ ክፍል ፡ ታስዕ ፡ በእንተ ፡ አውሰቦ ፡ ለእንተ ፡ ፈትሑ ፡ ላዕሌሃ ፡ በርትዕ ፡ በገቢረ ፡ ዝሙት ፡ ወእንተ ፡ ድኅርዋ ፡ በዘይደሉ ፡ ለተድኅሮ ።

፳፻፷ ሥርዋጽ ፡ ተነግረ ፡ ውስተ ፡ ቀኖናተ ፡ ነገሥት ፡ ኢይደልዎ ፡ ለመኑሂ ፡ ከመ ፡ ያውስብ ፡ ብእሲተ ፡ ኅድገተ ፡ እምዝሙት ፡ በጕጕዓ ፡ አላ ፡ ይጽናሕ ፡ እስከ ፡ ትኔስሕ ፡ ወይጤየቅ ፡ ንስሓሃ ፡ ወሰምዐ ፡ ይከውንዋ ፡ አግዋሪሃ ። አሜሃ ፡ ይደሉ ፡ አውሰቦታ ፡ ዘእንበለ ፡ ካህናት ፡ በቅድመ ፡ ፩ ፡ ቀሲስ ፡ ወእኮ ፡ ኤጲስቆጶስ ።

፳፻፷፩ ክፍል ፡ ዓሥር ፡ ተደምሮ ፡ ምስለ ፡ ፪ቱ ፡ አውሰቦ ፡ አው ፡ ዘይበዝኅ ።

፳፻፷፪ ክፍል ፡ ፲ወ፩ዱ ፡ አውሰቦ ፡ ራብዕት ፡ ወዘይልዕል ፡ እምኔሃ ።



ሙም ፡ ከገንዘቧ ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡ ፳፫ ፡ ዓመት ፡ ከሆናት ፡ በኋላ ፡ ከሂሳብ ፡ ወገን ፡ የሚገባ ፡ አደራውን ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ እንዲያጋባት ፡ ይናገራል ።

፳፻፶፭ ስድስተኛ ፡ ክፍል ። የጌታ ፡ ሚስት ፡ ባሏ ፡ ነፃ ፡ ሳወጣው ፡ ባሪያ ፡ ሚስት ፡ ልትሆን ፡ መልካም ፡ አይደለም ።

፳፻፶፮ ሰባተኛ ፡ ክፍል ። በትሩፋቱ ፡ ላይ ፡ እንደሚጨምር ፡ ሁሉ ፡ ምእመን ፡ የእርሱ ፡ ወገን ፡ ያልሆነችውን ፡ አማኝ ፡ ያልሆነችውን ፡ ማግባት ፡ እንዳይገባ ፡ ይናገራል ።

፳፻፶፯ ስምንተኛ ፡ ክፍል ። ለጋብቻ ፡ ከሚያስፈልገው ፡ ሩካቤ ፡ የሚከለክለውን ፡ ይናገራል ። ይህም ፡ ከእናቱ ፡ ማኅፀን ፡ ጀምሮ ፡ በተፈጥሮው እንደ ፡ ስልብ ፡ ያለ ፡ ቢሆን ፡ ነው ። ይኸውም ፡ በተፈጥሮው ፡ የተናገርነው ፡ ሩካቤ ፡ የማይቻለው ፡ ነው ። ፈናፍንታም ፡ ነው ። ይኸውም ፡ የወንድና ፡ የሴት ፡ አካል ፡ አንድነት ፡ በአንድ ፡ ቦታ ፡ ያለበት ፡ ነው ። ሴትም ፡ ሩካቤ ፡ የሚከለክል ፡ ትርፍ ፡ አጥንት ፡ ያለባት ፡ ብትሆን ፡ ነው ።

፳፻፶፰ ድንገተኞች ፡ ግን ፡ ፪ ፡ ወገን ፡ ናቸው ። ከእነርሱም ፡ አንዱ ፡ ስልብ ፡ ሁለተኛውም ፡ አእምሮ ፡ የጎደለው ፡ እብድ ፡ ፪ኛውም ፡ የሚቆራርጡ ፡ ደዌያት ፡ እንደ ፡ ደዌ ፡ ሥጋ ፡ ያሉ ፡ ናቸው ። ስለ ፡ ለምጽ ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡ ይሁን ። እነሆ ፡ የዚህን ፡ ክፍል ፡ ሥራት ፡ ጋብቻን ፡ በሚከለክለው ፡ ምዕራፍ ፡ ተናግረናል ።

፳፻፶፱ ዘጠኝኛ ፡ ክፍል ። በዝሙት ፡ ሥራ ፡ በአግባብ ፡ የፈረዱባትን ፡ ለመፈታት ፡ በሚገባ ፡ የፈቷትንም ፡ ማግባት ፡ እንዳይገባ ፡ ይናገራል ።

፳፻፷ ሥርዋጽ ፡ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ተነገረ ። የተፈታችውን ፡ ሴት ፡ በችኮላ ፡ ሊያገባ ፡ ለማንም ፡ አይገባውም ። እስክትመለስ ፡ በንስሓም ፡ መመለሷ ፡ እስኪረጋገጥ ፡ ጐረቤቶቿም ፡ እስኪመሰክሩላት ፡ ድረስ ፡ ይጠብቅ ፡ እንጂ ። ያን ጊዜ ፡ ያለብዙ ፡ ካህናት ፡ በአንድ ፡ ቄስ ፡ ፊት ፡ ሊያገባት ፡ ይገባል ።

፳፻፷፩ አሥረኛ ፡ ክፍል ። በሁለተኛው ፡ ወይም ፡ በሚበዛው ፡ ጋብቻ ፡ መሰብሰብ ፡ እንዳይገባ ፡ ይናገራል ።

፳፻፷፪ አሥራ ፡ አንደኛ ፡ ክፍል ። አራተኛ ፡ ከርሱ ፡ የሚበዛም ፡ ማግባት ፡ እንዳይገባ ፡ ይናገራል ።

አንቀጽ ፡ ፳፱ ።

፰፻፹፫ ፲ወ፪ቱ ፡ አውስቦ ፡ መንከሳይያት ።

፰፻፹፬ ፲ወ፫ቱ ፡ አውስቦ ፡ ዘኑለፈ ፡ እመዋዕሊሃ ፡ ፳ ፡ ዓመት ።

፰፻፹፭ ፲ወ፬ቱ ፡ አውስቦቱ ፡ እንተ ፡ ኢፈጸመት ፡ ዕድሜ ፡ ኀዘን ፡ ሞተ ፡ ምታ ፡ ወይእቲ ፡ ዓመት ፡ ፍጽምት ፡ እው ፡ ፲ቱ ፡ አውራኅ ፡ እሞተ ፡ ምታ ። ወዘአውስበ ፡ እምቅድመ ፡ ዝንቱ ፡ ዕድሜ ፡ ይትከላእ ፡ እምርስተ ፡ ብእሲቱ ፡ ወብእሲትኒ ፡ እምታ ፡ ወእምዘተአዘዘ ፡ ሎቱ ፡ ወላቲ ። ወዝንቱ ፡ ኑኀት ፡ ይከልእ ፡ እምአውስቦ ፡ ወኢይከልእ ፡ እምሕፃ ፡ ወኢእምፍኅረት ፡ ወባሕቱ ፡ ይኩን ፡ በጸሎት ።

፰፻፹፮ ፲ወ፭ቱ ፡ ለእመ ፡ ኢሠምሩ ፡ ለለ ፡ ፩ዱ ፡ እምብእሲ ፡ ወብእሲት ፡ ለአስተዋስቦ ፡ ካልእ ፡ አው ፡ ለእመ ፡ ሠምረ ፡ በዝንቱ ፡ ግብር ፡ በንግሥ ፡ ገጽ ፡ ዘ፩ዱ ፡ እምገጸተ ፡ ተመውአ ፡ ወሙእቱ ፡ በእንተ ፡ እንብር ፡ ፩ዱ ፡ እምገጸተ ፡ ትዕግልት ። ፪ቱ ፡ ክፍል ፡ ቀዳማዊ ፡ ዘእንበለ ፡ ምክሩ ፡ ለዘውእቱ ፡ ሀለወ ፡ ታሕተ ፡ ምልክናሁ ፡ ኢይኩን ፡ ሕፃሁ ፡ ወኢይኩን ፡ ተዋስቦ ፡ ዘእንበለ ፡ በሥምረተ ፡ ከልኢሆሙ ፡ እለ ፡ ይትዌሰቡ ። ወበሥምረተ ፡ እለ ፡ እሙንቱ ፡ ታሕተ ፡ ምግብናሆሙ ፡ ወዝንቱኒ ፡ ይከልእ ፡ እምአውስቦ ፡ ወጸሎተ ፡ ስብሳብ ፡ ወኢይከልእ ፡ እምፍፍኅረት ፡ ወሕፃ ። ወካልእ ፡ ክፍል ፡ ኢይደሉ ፡ ለሊተ ፡ ሀገር ፡ ወኢለመኳንንቲሃ ፡ ወኢለደቂቅ ፡ ወኢለ፩ዱሂ ፡ እምእሊአሆሙ ፡ ከመ ፡ ይፍኅሩ ፡ እሐተ ፡ እምኔሆን ፡ በረድኤት ። ወከማሁ ፡ ካዕበ ፡ ለእመ ፡ ኢበጽሐ ፡ አካለ ፡ ፍጻሜሃ ፡ ወዝንቱኒ ፡ ኢይከልእ ፡ እምፍኅረት ፡ ወሕፃ ።

፰፻፹፯ ክፍል ፡ ራብዕ ፡ ጠስ ፡ ፬ቱ ፡ ወለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ፈኀረ ፡ አው ፡ ዘተፋኅረት ፡ ምንትኒ ፡ እምድኅረ ፡ ወበበ ፡ ሕፃ ፡ ይደልዎ ፡ ለፈኀረ ፡ ከመ ፡ ይንግእ ፡ ዘወሀበ ፡ ቅድመ ፡ ወለፍኅረቲኒ ፡ ከመ ፡ ታግብእ ፡ ዘነሥአቶ ፡ ዘእንበለ ፡ ካዕበት ።

፰፻፹፰ ክፍል ። ወእቅድሞተ ፡ ሕፃስ ፡ ወፍኅረት ፡ በእንተ ፡ አውስቦ ፡ ዝኒ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ሥምረት ፡

ስለ ፡ ጋብቻ ።

፰፻፹፫ እሥራ ፡ ሁለተኛው ፡ መንከሳዪያትን ፡ ማግባት ፡ እንዳይገባ ፡ ይናገራል ።

፰፻፹፬ ፲፫ኛው ፡ ዕድሜዋ ፡ ከ፳ ፡ ዘመን ፡ ያለፈውን ፡ ማግባት ፡ እንዳይገባ ፡ ይናገራል ።

፰፻፹፭ ፲፬ኛው ፡ የባሏን ፡ ሞት ፡ የኀዘን ፡ ወራትን ፡ ያልፈጸመች ፡ ሴት ፡ ማግባት ፡ እንዳይገባ ፡ ይናገራል ። ይችውም ፡ ሙሉ ፡ ዓመት ፡ ወይም፡ ባሏ ፡ ከሞተ ፡ ጀምሮ ፡ ፲ ፡ ወር ፡ ናት ። ከዚህ ፡ ወራት ፡ አስተድሞ ፡ ያገባ ፡ ከሚስቱ ፡ ርስት ፡ ይከልከል ። ሴትም ፡ ከባሏ ፡ ርስት ። እርሱም ፡ እርሷም ፡ ከተዘዘላቸው ። ይህ ፡ የቀን ፡ ርዝመት ፡ ከመጋባት ፡ ይከለክላል ፡ ከመተጫጨትና ፡ ቃል ፡ ከማሰር ፡ አይከለክልም ። ነገር ፡ ግን ፡ በጸሎት ፡ ይሁን ።

፰፻፹፮ ፲፭ኛው ፡ ከወንድና ፡ ከሴት ፡ እያንዳንዱ ፡ ካልወደዱ ፡ ሌላ ፡ ሊያጋባቸው ፡ እንዳይገባ ፡ ይናገራል ። ወይም ፡ ድል ፡ ከመንሣት ፡ ግብራት ፡ ወገን ፡ አንዱን ፡ በመያዝ ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ ቢወድ ፡ ይኸውም ፡ ከቅሚያ ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ፡ ስለማገበር ፡ የሚናገር ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ፪ ፡ ክፍል ፡ ነው ። መጀመሪያው ፡ ከሞግዚትነቱ ፡ ስር ፡ ካለበት ፡ ሰው ፡ ምክር ፡ በስተቀር ፡ መተጫጨት ፡ እንዳይሆን ፡ ይናገራል ። ጋብቻ ፡ የሚጋቡት ፡ የሁለቱ ፡ ፈቃድ ፡ እነርሱ ፡ ከሥልጣናቸው ፡ በታች ፡ ባሉ ፡ በሞግዚቶችም ፡ ፈቃድ ፡ ካልሆነ ፡ በስተቀር ፡ አይደረግ ። ይህም ፡ ከጋብቻ ፡ ተክሊል ፡ ከማድረስ ፡ ይከለክላል ። ከመተጫጨት ፡ ማጫ ፡ ከመስጠት ፡ አይከለክልም ። ሁለተኛ ፡ ክፍል ። ለሀገር ፡ አሳዳሪ ፡ ለመኳንንቱ ፡ ለልጆቹ ፡ ከእርሱ ፡ ወገኖች ፡ ለአንዱ ፡ ከእነርሱ ፡ እንዲቱን ፡ በእርዳታ ፡ ሊያጩት ፡ እንዳይገባ ፡ ይናገራል ። እካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰችም ፡ ከሆነ ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ከመተጫጨት ፡ አይከለክልም ።

፰፻፹፯ ፬ኛ ፡ ክፍል ፡ ጠስ ፡ ፬ ። ያጨ ፡ ወይም ፡ የታጨች ፡ ማጫ ፡ ከሰጠ ፡ በኋላ ፡ ምንኩስናን ፡ ቢወድ ፡ አጭታው ፡ አስቀድሞ ፡የሰጣትን ፡ ማጫ ፡ ሊወስድ ፡ ይገባዋል ። እጮኛውም ፡ የወሰደችውን ፡ ያለትርፍ ፡ ልትመልስ ፡ ይገባል ።

፰፻፹፰ ክፍል ፡ አስተድሞ ፡ መተጫጨትና ፡ ማጫ ፡ መስጠት ፡ ግን ፡ ስለማግባት ፡ ነው ። ይኸ

አንቀጽ ፡ ፳፱ ።

ቦቱ ፡ በምክር ፡ ፍጹም ፡ ወበእንተ ፡ ኅሠሣ ፡ ዘሎ ፡ በኑኅ ፡ መዋሰል ፡ ዘተዓዲወ ፡ እንተ ፡ ቦቱ ። ተሰንእወ ፡ ከመ ፡ ትጽናዕ ፡ ፍቅሮሙ ፡ ምስለ ፡ አሆ ፡ ብሂሎቶሙ ። ወከመ ፡ ይትዐቀብ ፡ ወሪዛ ፡ ዘተሰንእወ ፡ በእንቲአሁ ፡ እስከ ፡ ይበጽሕ ፡ ለመጠን ፡ እካል ፡ ከመ ፡ ኢይቅድም ፡ እምኔሃ ፡ ወከመ ፡ ይኩን ፡ ተስፋ ፡ እውስቦ ፡ ንጹሕ ፡ ረዳኢ ፡ በእንተ ፡ ዐቀበ ፡ ንጽሕ ፡ ወከመ ፡ ይሚጥ ፡ ጸሕቀተ ፡ በዘከኑ ፡ ሰደሚ ፡ ለእስተጻልዎተ ፡ ዘይትፈቀድ ፡ ለመፍቅደ ፡ መርዓ ፡ ወያጽንዖ ፡ ፍቅረ ፡ በእንተ ፡ ተደምሮ ፡ ወይትሉ ፡ ትእዛዘ ፡ ፈጣሪ ፡ ጠቢብ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ። እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይቤ ፡ ኢይሜኔ ፡ ከመ ፡ ይንበር ፡ ብእሲ ፡ ባሕቲቱ ፡ ዳእሙ ፡ ንግበር ፡ ሎቱ ፡ ረድኤተ ፡ በአምሳሊሁ ፡ ቅድመ ፡ አስሬወ ፡ ወእምዝ ፡ ገብረ ።

፳፻፷፱ ምዕራፍ ፡ ሣልስ ። በእንተ ፡ ፍኅረት ፡ ወውእቱ ፡ ላዕለ ፡ ፪ቱ ፡ እክፋል ። ክፍል ፡ ቀዳማዊ ፡ በእንተ ፡ ውሳኔ ፡ ፍኅረት ፡ ወትእዛዛቲሁ ። ወስ ፡ ፩ዱ ፡ ፍኅረስ ፡ ኪዳን ፡ ውእቱ ፡ ወተስፋ ፡ ዘይቀድም ፡ እምእውስቦ ፡ ወይከውን ፡ በመጽሐፈ ፡ መልእክት ፡ ወዘእንበለ ፡ መጽሐፍ ።

፳፻፸ መጀ ፡ ፩ዱ ፡ ወግብረ ፡ እስተጻንዖ ፡ በዘንቱ ፡ ከመ ፡ ያስተጻንዕ ፡ ፍኅረተ ፡ በቅድመ ፡ ፪ቱ ፡ ካህናት ፡ እምአሰናግ ፡ በአንብሮተ ፡ እድ ፡ ወበመስቀል ፡ ኅተሚ ፡ ወሕልቀት ፡ ወይሥርዑ ፡ ከዋኒ ፡ ሕዝ ፡ ወይጽሐፉ ፡ በመጽሐፍ ፡ ወበተስናእዎቶሙ ፡ ለእለ ፡ ይትረከቡ ፡ ወበተሰናዎተ ፡ ሐዛኒቱ ፡ ወለዘኒ ፡ ሀለወት ፡ ይእቲ ፡ ታሕተ ፡ ምግቡ ። ወለእመ ፡ ኢይትመየጥ ፡ ቃሉ ፡ ብወሕ ፡ ላቲ ፡ ከመ ፡ ትትመየጥ ፡ ለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ከመ ፡ ይፍኅሬ ፡ ለዘውእቱ ፡ ዘኢኮነ ፡ ይሉወ ፡ ላቲ ፡ ወዘይከውና ፡ ሕሠመ ።

፳፻፸፩ ወይቲቀ ፡ ዝንቱኒ ፡ እለ ፡ አልቦሙ ፡ ልብ ፡ ወለእመኒ ፡ ኮኑ ፡ ምስለ ፡ ሐዛኒት ፡ ኢይፍቅዱ ፡ ኅበ ፡ ኅብረተ ፡ አበዊሆሙ ፡ በጊዜ ፡ ያስተዋስቦሙ ፡ ወኢ ፡ በጊዜ ፡ ፍኅረቶሙ ፡ ወባሕቱ ፡ ዝንቱ ፡ ይኩን ፡ በትእዛዝ ፡ ፈታሒ ።

፳፻፸፪ መከ ፡ ፶፱ቱ ፡ ወይደሉ ፡ እንከ ፡ እውስቦ ፡ ዘእንበለ ፡ ትልወት ፡ ወኪሕዓ ።

ስለ ፡ ጋብቻ ።

ውም ፡ በቁርጥ ፡ ሐሳብ ፡ ፈቃድ ፡ ይሆንበት ፡ ዘንድ ፡ ነው ። እሺ ፡ ከማለታቸውም ፡ ጋራ ፡ ፍቅራቸው ፡ ትጸና ፡ ዘንድ ፡ በተስማሙበት ፡ በቀጠሮው ፡ ቀን ፡ ርዘመት ፡ ሁሉን ፡ ስለመፈ ፈለግ ፡ ነው ። ስለ ፡ እርሱ ፡ የተስማሙለት ፡ (ያጩስት) ፡ ጎልማሳ ፡ እካለ ፡ መጠን ፡ እስኪያ ደርስ ፡ በእርሷ ፡ እንዳይቀድም ፡ ይጠበቅ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ንጹሕ ፡ ረዳት ፡ የሆነ ፡ የጋብቻ ፡ ተስፋም ፡ ንጽሕናን ፡ ስለመጠበቅ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ነው ። በዚያ ፡ ወራትም ፡ ለሥርጉ ፡ መፍቅድ ፡ (ጣጣ) ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ወደ ማዘጋጀት ፡ ሐሳቡን ፡ ይመልስ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ስለመገናኘት ፡ ፍቅርን ፡ ያጸና ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ከብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባውና ፡ የጠቢብ ፡ ፈጣሪ ፡ ትእዛዝን ፡ ይከተል ፡ ዘንድ ፡ ነው ። እርሱ ፡ የምትመስለውን ፡ ረዳት ፡ እንፍጠርለት እንጂ ፡ ሰው ፡ ብቻውን ፡ ሊኖር ፡ አይገባም ፡ ብሏልና ። አስተድሞ ፡ ተስፋ ፡ ሰጠ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ፈጠረ ።

፳፻፷፱ ፪ኛው ፡ ምዕራፍ ፡ ስለማጨት ፡ ይናገራል ። እርሱም ፡ በ፪ ፡ የተከፈለ ፡ ነው ። መጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ ስለማጨትና ፡ ስለሁሉ ፡ ውሳኔ ፡ ነው ። ጠስ ፡ ፩ ። ማጨትስ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ መጋባትና ፡ ከጋብቻ ፡ የሚቀድም ፡ ተስፋ ፡ ነው ። በደብ ዳቤ ፡ ያለደብዳቤም ፡ ይሁን ።

፳፻፸ መጀ ፡ ፩ ። ይህንም ፡ የማጽናት ፡ ግብር ፡ ከሽ ማግሌች ፡ ወገን ፡ በሁለት ፡ ካህናት ፡ ፊት ፡ እጅ ፡ በመጫን ፡ በሚያከብር ፡ መስቀል ፡ በተ ለበት ፡ መተጫጨትን ፡ ያጸኑ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። የመተጫጨትን ፡ ሁኔታ ፡ በሚገቡት ፡ ስምም ነትና ፡ በምግዚቲቱ ፡ ስምምነት ፡ ወስነው ፡ በደብዳቤ ፡ ይጻፉ ። ከሥልጣኑ ፡ በታች ፡ ያለ ችውንም ፡ ተስማሚ ፡ ለማይሆናትና ፡ ክፉ ፡ ለሚሆንባት ፡ ሊያጫት ፡ ቢወድ ፡ ቃሉም ፡ ባይ ለወጥ ፡ ለርሷ ፡ ቃሏን ፡ ትለውጥ ፡ ዘንድ ፡ ሥል ጣን ፡ አላት ።

፳፻፸፩ እእምሮ ፡ የሌላቸው ፡ የዝንጉዎች ፡ ልጆች ፡ ከሞግዚት ፡ ጋር ፡ ያሉ ፡ ቢሆኑ ፡ በሚያጩላ ቸውና ፡ በሚያጋቡዋቸው ፡ ጊዜ ፡ የአባቶቻቸ ውን ፡ አንድነት ፡ አይፈልጉ ። ነገር ፡ ግን ፡ በዳኛ ትእዛዝ ፡ ይሁን ።

፳፻፸፪ መከ ፡ ፶፱ ። እንግዲህ ፡ ያለ ፡ ትሎት ፡ ያለ ፡ ማጫ ፡ ማግባት ፡ ይገባል ።

አንቀጽ ፡ ፳፱ ።

፰፻፸፫ ጠስ ፡ ዘ፩ዱ ፡ ወዘ'ነዘንት ፡ በእንተ ፡ ብእሲሃ ፡ ኢትትከላእ ፡ እምፍንረት ፡ ወኢይፍንሩ ፡ ስዘ ኢኀለፈ ፡ መዋዕሊሁ ፡ እምኗቱ ፡ ዓመት ። ወለዘነፈረ ፡ ወኢሥርሀ ፡ ዕድሜ ፡ ውሉን ፡ ለአውስቦ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ህልወ ፡ ይኩን ፡ ዕድሜሁ ፡ ፪ቱ ፡ ዓመተ ፡ ወለእመ ፡ ነገደ ፡ ርኁቀ ፡ ይኩን ፡ ዕድሜሁ ፡ ፫ቱ ፡ ዓመተ ። ወለእመሰ ፡ ተወሰከ ፡ እምዝቱ ፡ ዕድሜ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ትትወሀብ ፡ ለካልእ ፡ ወይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ዕድሜ ፡ ፬ቱ ፡ ዓመተ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ በምክንያተ ፡ ዕዉቅ ፡ ዘከመ ፡ ደዌ ፡ አው ፡ ፈድፋ ፡ ዕፃ ፡ አው ፡ አበሳ ፡ ዘይደሉ ፡ ለሞት ፡ አው ፡ ንግደት ፡ ርኅቅት ፡ እንተ ፡ ኮነት ፡ በእንተ ፡ ኅጸበ ።

፰፻፸፬ ወለአብ ፡ ይደልዎ ፡ ለሊሁ ፡ ከመ ፡ ይፍታሕ ፡ ፍንረተ ፡ ለእንተ ፡ ሀለወት ፡ ታሕተ ፡ ሥልጣኑ ፡ ወአኮ ፡ ለእንተ ፡ ትነብር ፡ ታሕተ ፡ ሥልጣና ።

፰፻፸፭ ወኢይደልዎ ፡ ለዘአማዕተበዎ ፡ ከመ ፡ ይፍታሕ ፡ ዘነዋ ፡ ኮነ ፡ ፈንሩ ።

፰፻፸፮ መጀ ፡ ዘ፩ዱ ፡ ወለእመሰ ፡ ኮኑ ፡ እለ ፡ ይትዋሰቡ ፡ ድክተማን ፡ ወኢብጹሓን ፡ አምጣነ ፡ ወአልቦ ፡ አብ ፡ ለ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ወኢእም ፡ ወኢእዘዚ ፡ ወፈንሩ ፡ ንፍሳቲሆሙ ፡ በቅድመ ፡ ሰብእ ፡ ወለእመ ፡ ኀዘኑ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ለይንበሩ ፡ እስከ ፡ ይበጽሑ ፡ ፲ወ፰ተ ፡ ዓመተ ፡ ወለእመ ፡ ኢይደሉ ፡ ለ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ይሴሲ ፡ ካልእ ፡ በእንተ ፡ ኀጢአ ፡ ሥርዓቶሙ ። ወለእመ ፡ ፈጸሙ ፡ ጐልቈ ፡ ዝንቱ ፡ ዓመት ፡ ወመልአ ፡ ልቡናሆሙ ፡ ይኩን ፡ ሎሙ ፡ ከመ ፡ ይግበሩ ፡ ዘረትዑ ፡ እመኒ ፡ ኀብረተ ፡ ወእመኒ ፡ ፍልጠተ ።

፰፻፸፯ ዘስንቀራ ፡ ፲ቱ ፡ ለወለት ፡ እንተ ፡ ሀለወት ፡ ውስተ ፡ ሕፅን ፡ ወላድያኒሃ ፡ አው ፡ በሥልጣነ ፡ ዚአሃ ፡ ወፈንራ ፡ ፩ዱ ፡ ብእሲ ፡ ለርእሱ ፡ ወአሀ ትቢሎ ፡ ለተዋስቦ ፡ ወበልዑ ፡ ወሰትዩ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ወእምዝ ፡ አኀዛ ፡ እምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ተዓጋሊ ፡ ወነሥአ ፡ በግብር ። አው ፡ በጕሕሉት ፡ ወተደመረ ፡ ትትመየጥ ፡ ኀበ ፡ ዘፈንራ ፡ ቀዳሚ ፡ በዘኮነ ፡ ከዊና ፡ በምንትኒ ፡ ግብር ፡ ለእመ ፡ ይሬትድ ፡ ውእቱ ። ወለእመሰ ፡ ኢፈቀደ ፡ ይደልዎ ፡ ለተዓጋሊ ፡ ከመ ፡ ያውስባ ፡ ለእመ ፡ አልቦቱ ፡ ብእሲት ።

ስለ ፡ ጋብቻ ።

፰፻፸፫ ጠስ ፡ ፩ ። በባሏ ፡ ምክንያት ፡ ያዘነች ፡ ሴት ፡ ከመታጨት ፡ አትከልከል ። ዕድሜው ፡ ከ፳ ፡ ዓመት ፡ ላላለፈ ፡ ሕፃን ፡ አይጨበጡት ። ሚስት ፡ አጭቶ ፡ የሠርጉን ፡ ቀን ፡ ያልወሰነ ፡ ሰው ፡ በሃገር ፡ ያለ ፡ ቢሆን ፡ ቀጠሮው ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ይሁን ። ወደሩቅ ፡ ሃገር ፡ የሄደ ፡ ቢሆን፡ ቀጠሮው ፡ ፫ ፡ ዓመት ፡ ይሁን ። ከዚች ፡ ቀጠሮ ፡ ቢበልጥ ፡ ግን ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ልትሰጥ ፡ ይገባል ። ቢታወቅ ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ቀጠሮው ፡ ፬ ፡ ዓመት ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ። ይኸውም፡ እንደ ፡ መታመም ፡ ወይም ፡ ዕዳ ፡ እንደ ፡ መክፈል ፡ ወይም ፡ ለሞት ፡ እንደሚያበቃ ፡ ወንጀል ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ጭንቅ ፡ የሆነች ፡ ሩቅ ፡ ሀገር ፡ እንደ ፡ መሄድ ፡ ያለ ፡ ነው ።

፰፻፸፬ አባት ፡ በራሷ ፡ ሥልጣን ፡ ለምትኖረው ፡ ያይደለ ፡ በእርሱ ፡ ሥልጣን ፡ ለምትኖረው ፡ ልጁ ፡ ውልን ፡ ሊሽር ፡ ይገባዋል ።

፰፻፸፭ ለሞግዚት ፡ እጮኛዋን ፡ ሊያሰናብት ፡ አይገባውም ።

፰፻፸፮ መጅ ፡ ፩ ፡ የሚጋቡት ፡ ልጆች ፡ ደኃ ፡ አደጎች ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሱ ፡ ቢሆኑ ፡ ከእነርሱ ፡ ወገን ፡ ለአንዱ ፡ አባት ፡ እናት ፡ ሞግዚት ፡ ባይኖረው ፡ ራሳቸው ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ ቢተጫጨ ፡ ስለዚህም ፡ ቢያዝኑ ፡ ፲፰ ፡ ዓመት ፡ እስኪመላቸው ፡ ይቆዩ ። ከእነርሱ ፡ ወገን ፡ ለአንዱ ፡ እስተዳደራቸውን ፡ ባለማወቅ ፡ ሁለተኛውን ፡ ሊመግብ ፡ ባይችል ፡ የዚህን ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ቢፈጽሙ ፡ አእምሮአቸውም ፡ ትክክል ፡ ቢሆን ፡ አብረው ፡ ቢኖሩም ፡ ቢለያዩም ፡ የወደዱትን ፡ ሊያደርጉ ፡ ይገባቸዋል ።

፰፻፸፯ ስንቀራ ፡ ፲ ። በወላጆቿ ፡ ሥልጣን ፡ ወይም ፡ በራሷ ፡ ሥልጣን ፡ ያለችውን ፡ ልጅ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ለራሱ ፡ ቢያጫት ፡ ሊጋብቻም ፡ እሺ ፡ ብትለው ፡ አብረው ፡ (ቢት ፡ ማያ) ፡ ቢበሉ ፡ ቢጠጡ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቀማኛ ፡ ቢይዛት ፡ በግድ ፡ ወይም ፡ በተንኮል ፡ ነጥቆ ፡ ቢደርስባት ፡ የሆነ ፡ ሁኖ ፡ በማናቸውም ፡ ነገር ፡ እርሱ ፡ ከፈቀደ ፡ ቀድሞ ፡ ወደአጫት ፡ ሰው ፡ ትመለስ ። ባይወድ ፡ ግን ፡ ቀማኛው ፡ ሰው ፡ ሚስት ፡ ከሌለችው ፡ እርሱ ፡ ሊያገባት ፡ ይገባዋል ።

አንቀጽ ፡ ፳፱ ።

፫፻፸፰ ሥርዋጽ ፡ ይብል ፡ በቀኖናተ ፡ ኤጲፋንዮስ ፡ ወካልአኒሁ ፡ ዘይዜሙ ፡ በወለት ፡ ድንግል ፡ ኢያስተዋስብዎ ፡ ኪያሃ ፡ ለእመ ፡ ኢኀደጋ ፡ ፈኀሪሃ ፡ ዘቀዳሚ ፡ ለእመ ፡ ኮነት ፡ ፍኅርተ ፡ ወለእመሰ ፡ ኢተፋኀረት ፡ ይኩን ፡ በሥምረት ፡ ሰብአ ፡ ቢአሃ ፡ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ያውስብ ፡ ኪያሃ ፡ በግብር ፡ ወለእመኒ ፡ ኮነት ፡ ንዳዩተ ፡ ወሕሥምተ ፡፡

፫፻፸፱ ክፍል ፡ ዳግም ፡ በእንተ ፡ ዓረቦን ፡ ዘፍኅረት ፡፡ ጠስ ፡ ፪ቱ ፡ ዓረቦንሰ ፡ ዘበእንቲአሁ ፡ ውእቱኬ ፡ እምከመ ፡ አበየ ፡ ነሚኢሁ ፡ እምድኅረ ፡ ተመጠወ ፡ ኪያሁ ፡ ወገደፋ ፡ ለተሰናእዎ ፡ ይሚጥ ፡ ዘአኀዘ ፡ ገቢሮ ፡ ካዕበተ ፡፡ ወእመ ፡ አበየ ፡ ወሃቢሁ ፡ ለዐረቦን ፡ ይደቅ ፡ ዓረቦን ፡ ዘወሀቦ ፡፡

፫፻፹ ወለእመሰ ፡ ኮነ ፡ ምክንያተ ፡ ሞት ፡ ተዳደቆ ፡ ቦ ፡ ውስቴቱ ፡ ፪ቱ ፡ ቃላት ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ጠስ ፡ ፪ቱ ፡ ይሚጥ ፡ ዘነሥአ ፡ ለእመ ፡ ኢኮነ ፡ ዘሞተ ፡ ውእቱ ፡ ምክንያተ ፡ ተድኅሮ ፡ ዘፍጻሜ ፡ ኩብካብ ፡፡

፫፻፹፩ ወዳግማዊ ፡ ዘይጸንዕ ፡ ውእቱ ፡፡ መጽ ፡ ፶ወ፫ቱ ፡ ወእመሰ ፡ ሞተት ፡ ይእቲ ፡ ብእሲት ፡ ለያግብእ ፡ ፈኀሪሃ ፡ እምሰብአ ፡ ቢአሃ ፡ ዘወሀበ ፡ በእንቲአሃ ፡ ዘእንበለ ፡ መብልዕ ፡ ወመስቴ ፡ ዘወሀበ ፡፡ ወለእመሰ ፡ ሞተ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ዘሎቱ ፡ ሕዝ ፡ ወአልቦቱ ፡ ወራሲ ፡ ይኅድጉ ፡ ላቲ ፡ ዘነሥአት ፡ እምኔቤሁ ፡ እስመ ፡ ላቲ ፡ ይደልዋ ፡ እምካልአን ፡ በእንተ ፡ ሞቱ ፡ ምታ ፡ ለወለት ፡ ሕፅይት ፡፡ ወእመሰ ፡ ቦቱ ፡ ወራስያን ፡ ያግብኡ ፡ ሎሙ ፡ መንፈቀ ፡ ንዋዩ ፡ ወመንፈቀ ፡ ይትረፍ ፡ ላቲ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ተዋስቦቶሙ ፡ በጥዩቅ ፡፡

፫፻፹፪ ጠስ ፡ ፪ቱ ፡ ወለዘሂ ፡ ተሠርዐ ፡ በሕይወተ ፡ አብ ፡ ወሠምረ ፡ ቦቱ ፡ ኢይጠልቀዎ ፡፡ ወእመኒ ፡ አቡሃ ፡ ለወለት ፡ አው ፡ እማ ፡ ነሥኡ ፡ ዓረቦነ ፡ አው ፡ እምኔሁ ፡ ዘአሃ ፡ በእንተ ፡ ወለተ ፡ ወልዱ ፡ ወኮነ ፡ መዋዕሊሆሙ ፡ ዘበጽሑ ፡ ለመጠነ ፡ አክል ፡ ይንሥኡ ፡ ምክዕቢተ ፡ ለእመ ፡ ኮኑ ፡ ዘይትከሀሎሙ ፡ ገቢረ ፡ መርዓ ፡ ወአበዩ ፡ ገቢሮቶ ፡፡ ወእመሰ ፡ ኮኑ ፡ ዘኢይትከሀሎሙ ፡ ሊያግብኡ ፡ ዓረቦነ ፡ ዘእንበለ ፡ ካዕበት ፡፡ ወበዝንቱ ፡ ፍትሕ ፡ ይኩን ፡ ግብር ፡ ለዘነሥአ ፡ እማ

ስለ ፡ ጋብቻ ፡፡

፫፻፸፰ ሥርዋጽ ፡፡ በኤጲፋንዮስና ፡ በሌሎች ፡ መጻሕፍት ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡፡ በድንግሊቱ ፡ ልጅ ፡ የሰሰነ ፡ ሰው ፡ የታጨች ፡ ከሆነች ፡ የቀድሞ ፡ እጮኛዋ ፡ ካልተዋት ፡ እርሷን ፡ አያጋቡት ፡፡ ያልታጨች ፡ ከሆነች ፡ ግን ፡ በቤተሰቦቿ ፡ ፈቃድ ፡ ይሁን ፡፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ድኻም ፡ ብትሆን ፡ መልክ ፡ ጥፉም ፡ ብትሆን ፡ በግድ ፡ ርሷን ፡ ያግባ ፡፡

፫፻፸፱ ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ስለመተጫጫው ፡ ዐረቦን ፡ ይናገራል ፡፡ ጠስ ፡ ፪ ፡ ስለርሱ ፡ (ስለመተጫጨት) ፡ የሚሆን ፡ ዐረቦን ፡ ግን ፡ ዐረቦኑን ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ ተቀባዩ ፡ እንቢ ፡ ቢል ፡ ውሉንም ፡ ቢያፈርስ ፡ የተቀበለውን ፡ ዕጥፍ ፡ አድርጎ ፡ ይመልስ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡፡ ዐረቦን ፡ ሰጭው ፡ እንቢ ፡ ቢል ፡ ግን ፡ የሰጠው ፡ ዐረቦን ፡ ይቅርበት ፡፡

፫፻፹ የሞት ፡ ምክንያት ፡ ድንገት ፡ ቢያገኘው ፡ ግን ፡ በውስጡ ፡ ሁለት ፡ ነገሮች ፡ አሉ ፡፡ ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ ጠስ ፡ ፪ ፡፡ ሠርጉ ፡ የሚፈጸምበት ፡ ቀን ፡ በመቆየቱ ፡ ምክንያት ፡ እርሱ ፡ የሞተ ፡ ካልሆነ ፡ የወሰደውን ፡ ይመልስ ፡፡

፫፻፹፩ ሁለተኛው ፡ የሚጸና ፡ ነው ፡፡ መጽ ፡ ፶፫ ፡፡ ይህች ፡ ሴት ፡ ብትሞት ፡ ግን ፡ እጮኛዋ ፡ ከተበላውና ፡ ከተጠጣው ፡ በቀር ፡ ስለእርሷ ፡ የሰጠውን ፡ ከቤተ ፡ ሰቦቿ ፡ መልሶ ፡ ይውሰድ ፡፡ ማጫ ፡ የሰጠው ፡ ሰው ፡ ቢሞት ፡ ግን ፡ ወራሽም ፡ ከሌለው ፡ ከእርሱ ፡ ዘንድ ፡ የወሰደችውን ፡ ማጫ ፡ ይተዉላት ፡፡ ባሏ ፡ ስለሞተ ፡ ከሌሎች ፡ ይልቅ ፡ ለታጨችቱ ፡ ልጅ ፡ ለርሷ ፡ ይገባታልና ፡፡ ወራሾች ፡ ቢኖሩት ፡ ግን ፡ የገንዘቡን ፡ እኩሌታ ፡ ይመልሱላቸው ፡፡ እኩሌታው ፡ ግን ፡ መጋባታቸው ፡ እውነት ፡ ከሆነ ፡ ይቅርላት ፡፡

፫፻፹፪ ጠስ ፡ ፪ ፡፡ አባት ፡ በሕይወት ፡ ሳለ ፡ የተሠራውን ፡ የተስማማበትን ፡ አይለውጡት ፡፡ የልጂቱ ፡ አባት ፡ ወይም ፡ እናቷ ፡ ወይም ፡ አያቷ ፡ ስለወንድ ፡ ልጁ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ዐረቦን ፡ ቢቀበሉ ፡ ልጆች ፡ በዕድሜያቸው ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያደረሱ ፡ ሆነው ፡ ሠርግ ፡ ማሠረግ ፡ ሲቻላቸው ፡ አናደርግም ፡ ቢሉ ፡ የወሰዱትን ፡ ማጫ ፡ ዕጽፍ ፡ አድርገው ፡ ይመልሱ ፡፡ የማይቻላቸው ፡ ቢሆኑ ፡ ግን ፡ ያለትርፍ ፡ ዐረቦኑን ፡ ይመልሱ ፡፡ ዐረቦኗን ፡ በተቀበለ ፡ በእርሷ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡

ዘኢ ፡ ዘሥሉጥ ፡ ላዕሌሃ ፡ ዓረቦን ፡ ዘእሃ ።

ባለው ፡ በሞግዚቱም ፡ ይህ ፡ ፍርድ ፡ ግዴ ፡ ይሁ ንበት ።

፰፻፹፫ ወፍጻሜ ፡ መጠነ ፡ እክሊል ፡ ዘእደው ፡ ፳ ፡ ዓመት ፡ ወእመ ፡ እስ ፡ ፳ወ፭ቱ ፡ ዓመት ። ወለ አንስትኒ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ዓመት ፡ ወእመ ፡ እስ ፡ ፲ወ፭ቱ ፡ ዓመት ።

፰፻፹፫ የወንዶች ፡ የአክሊል ፡ መጠን ፡ ፍጻሜ ፡ ኻያ ፡ ዓመት ፡ ያም ፡ ባይሆን ፡ ኻያ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ነው ። የሴቶችም ፡ ፲፪ ፡ ዓመት ፡ ያም ፡ ባይሆን ፡ ፲፭ ፡ ዓመት ፡ ነው ።

፰፻፹፬ ወአስስሎተ ፡ ምልክናሆሙ ፡ ለዘአመተብዎ ፡ ላዕ ሌሆሙ ፡ ይትገሠሥ ፡ እምፈቃዶሙ ፡ ከመ ፡ ያስስ ል ፡ እምኔሆሙ ፡ ሥልጣነ ፡ ምግባት ፡ በዘይበ ቍዖሙ ፡ ይሴመዩ ፡ ቦቱ ፡ ምግባሬቶሙ ፡ ወንዋዮሙ ። እስመ ፡ እሙንቱ ፡ በዝአይን ፡ ከመ ፡ ይሥርዑ ፡ ግብሮሙ ፡ ወንዋዮሙ ፡ ወከመ ይኩንዎሙ ፡ ስምዐ ፡ በዝንቱ ።

፰፻፹፬ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ የሾሙትን ፡ ሰው ፡ ሥልጣን ፡ ለማስወገድ ፡ ሥራቸውንና ፡ ገንዘባቸውን ፡ በሚጠቅማቸው ፡ ገንዘብ ፡ ያስተዳድሩበት ፡ ዘንድ ፡ የማስተዳደሩን ፡ ሥልጣን ፡ ከእነርሱ ፡ ላይ ፡ እንዲያነሣላቸው ፡ ከዳኛ ፡ ይጠይቁ ። ገን ዘባቸውንና ፡ ሥራቸውን ፡ ለማከናወን ፡ ብቁ ዎች ፡ ናቸውና ፡ በዚህም ፡ ምስክር ፡ ይሆኗ ቸው ፡ ዘንድ ።

፰፻፹፭ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ይግበሩ ፡ ዘተከሥተ ፡ ሎሙ ፡ በፈጽሞተ ፡ ምክር ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ፍኅረት ፡ እግነ ፡ ወውሂበ ፡ ዓረቦን ፡ ለፍኅረት ። ወእምድኅረዝ ፡ ሶበ ፡ አበየት ፡ ይእቲ ፡ ፍኅርት እምተደምሮ ፡ ምስለ ፡ ፈኀሪሃ ፡ በእንተ ፡ ሕመም ፡ ማእዝ ፡ ውስዝነ ፡ ስሕተተ ፡ አው ፡ በእንተ ፡ ዕልወት ፡ ሕግ ፡ ወተፈልጦ ፡ በፈቃደ ፡ ሕሊናሁ ፡ አው ፡ እመ ፡ ኮነ ፡ ውእቱ ፡ ዘኢይት ከሀሎ ፡ ከመ ፡ ይትራከብ ፡ ምስሌሃ ፡ ተራክቦተ ዘይበቍዕ ፡ ለወሊድ ፡ አው ፡ በካልእ ፡ ግብር ፡ ዘይደልዎ ፡ ተከልኦ ። ወእመሰ ፡ ቆመ ፡ ሰማዕ ታት ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ከመ ፡ ይእቲ ፡ ብእሲት ፡ ወወላድያኒሃ ፡ አእመሩ ፡ ዘንተ ፡ እምቅድመ ፡ ነሢአ ፡ ዓረቦን ፡ ኢየኀውሩ ፡ ዘእንበለ ፡ ነፍሳ ቲሆሙ ። ወለእመሰ ፡ ኢያእመሩ ፡ በዝንቱ ፡ ሶበ ፡ ተወከፉ ፡ ዓረቦን ፡ ጊዜ ፡ ፍኅረት ፡ አው ፡ ኮነ ፡ ግብር ፡ እምድኅረ ፡ ውሂበ ፡ ዓረቦን ፡ በም ንትኒ ፡ ምክንያት ፡ ዘይደልዎ ፡ ተኀስሖ ፡ ሶበ ሚጠ ፡ ዓረቦን ፡ ኢይትኀሠሥዎሙ ፡ ምክዕቢቶ ።

፰፻፹፭ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ምክር ፡ በመፈጸም ፡ የተገለጸላ ቸውን ፡ ያድርጉ ። መተጫጨት ፡ ለመተጫጨ ትም ፡ ዐረቦን ፡ መስጠት ፡ ሰውነት ፡ ከሆን ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይች ፡ ዕጮኛ ፡ ስለ ፡ ጠባዩ ፡ መጥፎነትና ፡ ስለ ፡ ስሕተቱ ፡ ብዛት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ አፍራሽነቱ ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ ስለ መለየቱ ፡ ወይም ፡ ልጅ ፡ ለመውለድ ፡ የሚጠ ቅመውን ፡ ሩካቢ ፡ ከእርሷ ፡ ጋራ ፡ ሊገኝ ፡ የማይችል ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ለመከልከል ፡ በሚ ያበቃ ፡ በሌላም ፡ ግብር ፡ ቢሆን ፡ ከዕጮኛዋ ፡ ጋራ ፡ ከመገናኘት ፡ እንቢ ፡ ብትል ፡ ይች ፡ ሴትና ፡ ወላጆቿ ፡ ዐረቦኑን ፡ ከመቀበላቸው ፡ አስቀድሞ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ እንዳወቁ ፡ ምስክ ሮች ፡ ስለዚህ ፡ ቢመሰክሩ ፡ ከራሳቸው ፡ በቀር ፡ አይንቀፉ ። በሚያጩበት ፡ ጊዜ ፡ ዐረቦኑን ፡ ሲቀበሉ ፡ ይህን ፡ ባያውቁ ፡ ግን ፡ ወይም ፡ ዐረቦኑን ፡ ከመስጠት ፡ በኋላ ፡ ለመመለስ ፡ በሚያበቃ ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፡ ግዴ ፡ ቢሆን ፡ ማጫውን ፡ በሚመልሱበት ፡ ጊዜ ፡ አጠፌታ ፡ አይፈልጉባቸው ።

፰፻፹፮ ክፍል ፡ ሣልስ ፡ በእንተ ፡ እምኃ ፡ እምቅድመ ፡ መርዓ ፡ ዘይከውን ። ጠስ ፡ ፫ቱ ፡ ኵሉ ፡ ብእሲ ፡ ዘወሀበ ፡ እምኃ ፡ ለፍጻሜ ፡ አውሰበ ፡ ለእመ ፡ ኢተፈጸመ ፡ ከዋኔ ፡ መርዓ ፡ ያግብእ ፡ ሎቱ ፡ እምኃሁ ።

፰፻፹፮ ፫ኛ ፡ ክፍል ፡ ከሠርግ ፡ በፊት ፡ ስለሚሆነው ፡ የእጅ ፡ መንሻ ፡ ይናገራል ። ጠስ ፡ ፫ ። ጋብቻን ፡ ለመፈጸም ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ የሰጠ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የሠርጉ ፡ አኳኋን ፡ ካልተፈጸመ ፡ እጅ ፡ መን ሻውን ፡ ይመልሱለት ።

፰፻፹፯ መክ ፡ ፺ወ፫ቱ ፡ ወለእመሰ ፡ ብእሲ ፡ ለሊሁ ፡ አበየ ፡ አውሰቦታ ፡ በፈቃዱ ፡ እንትኦስ ፡ ዓረ ቦን ፡ ዚአሁ ፡ ወኀደጎ ፡ ዘወሀበ ፡ ላቲ ፡ እምኃሁ ። ወእመሰ ፡ ኮነ ፡ እመ ፡ ንካለ ፡ ብእሲት ፡ ታግብእ ፡

፰፻፹፯ መክ ፡ ፺፫ ። ራሱ ፡ ሰውየው ፡ ማግባቱን ፡ እንቢ ፡ ቢል ፡ ግን ፡ ለእርሱዋ ፡ ዐረቦኑንና ፡ የሰጣት ፡ እጅ ፡ መንሻውን ፡ ሁሉ ፡ በፈቃዱ ፡ አጠፋ ። ብሴቲቱ ፡ ዘቀል ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ከዐረቦን ፡ ወገን ፡

ኵሎ ፡ ዘአኅዘት ፡ እምዓረቦን ፡ ወእምኅነሁ ፡ ዘወሀበ ፡ ታማብእ ፡ በከመ ፡ ዓረቦን ።

፰፻፹፰ ወስ ፡ ፫ቱ ፡ ወእምኅነሰ ፡ ለፍኅረት ፡ ውእቱ ፡ ወእኮ ፡ ለአውስቦ ፡ እስመ ፡ እምኔነ ፡ ዘትከውን ፡ በዕለተ ፡ መርዓ ፡ እመ ፡ ሀለወት ፡ ብእሲት ፡ በቤታ ፡ ይከውን ፡ ላቲ ፡ እምኔነ ፡ እስመ ፡ ፍኅረቲ ፡ ይእቲ ፡ ዘፈኀረ ፡ እምርኑቅ ። ወእመኒ ፡ ሀለወት ፡ በቤተ ፡ ብእሲ ፡ ትከውን ፡ እምኔነ ፡ ለብእሲት ። ወአብዕልተ ፡ እዳ ፡ ዘብእሲ ፡ ኢይነሥእ ፡ እምእምኔነ ፡ ዘወሀባ ፡ ለፍኅረቲ ፡ ምንተኒ ፡ እምንዋዩ ።

፰፻፹፱ ዘ፬ቱ ፡ ወብእሲትኒ ፡ ትቅድም ፡ ንሢአ ፡ ሕፃፃ ፡ ቅድመ ፡ አብዕልተ ፡ ሰዳ ፡ ዘምኑ ፡ ወኢትቅድም ፡ በእንተ ፡ እምኔነ ፡ ዘኮነ ፡ ቅድመ ፡ መርዓ ፡ እምአብዕልተ ፡ ሰዳ ፡ ተደማውያን ።

፰፻፺ ምስራፍ ፡ ራብዕ ፡ በእንተ ፡ ግብረ ፡ ወላዲ ፡ ምስለ ፡ ወልዱ ፡ በአውስቦ ፡ የሀብ ፡ በእንተ፡አሁ ከመ ፡ መስኪ ፡ ዘይትወፈይ ፡ ሀየንተ ፡ ዘሀለወ ፡ ታሕተ ፡ ሥልጣኑ ። ወስ ፡ ዘ፫ቱ ፡ ኢይደልዎ ፡ ለአብ ፡ አንብሮተ ፡ ወልዱ ፡ ለአውስቦ ፡ ለእመ ፡ ነበረ ፡ ወልዱ ፡ በንጽሕና ፡ እንዘ ፡ ሀለወ ፡ ታሕተ ፡ ሥልጣኑ ። ወእመሰ ፡ ኮነ ፡ ንዘሀሉለ ፡ በማብሩ ፡ ኢይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይእበዮ ፡ ትእዛዞ ።

፰፻፺፩ ዘ፭ወ፫ቱ ፡ ወለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ወላዲ ፡ ከመ ፡ ያስተዋስብ ፡ ወለቶ ፡ እው ፡ ወለተ ፡ ወልዱ ፡ እው ፡ ወለተ ፡ ወለቱ ፡ ወወሀበ ፡ ትልወታ ፡ በእምባነ ፡ ክሌሆቱ ፡ ወእመ ፡ አበየት ፡ እምድኅረ ፡ ዘንቱ ፡ ወረተደት ፡ ግብረ ፡ ሕሡመ ፡ ትስደድ ፡ እምርስቱ ።

፰፻፺፪ ዘ፩ቱ ፡ ወኢይደልዎሙ ፡ ለውሉድ ፡ ከመ ፡ ይንሥኡ ፡ አውስቦ ፡ በዘይኑ ፡ አሕሥሞ ፡ ዲበ ፡ ወላድያኒሆሙ ፡ ከመ ፡ ያብእዎሙ ፡ ውስተ ፡ ሰዳ ፡ በውሂበ ፡ ትልወት ፡ ወፈድየ ፡ እምኔነ ፡ እንተ ፡ ነሥኡ ፡ እምቅድመ ፡ መርዓ ። ወኢይደሉ ፡ ለወላድያን ፡ ከመ ፡ ይንሥኡ ፡ ሕገ ፡ አውስቦ ፡ በምንትኒ ፡ ሰጸብ ፡ በከዊኖቶሙ ፡ አበወ ፡ ወውሂቦቶሙ ፡ ትልወተ ፡ ወእምኔነ ፡ ዘይሁብዎ ፡ ቅድመ ፡ መርዓ ።

፰፻፺፫ ወዘሂ ፡ ይከልእ ፡ እለ ፡ ታሕተ ፡ ሕሰኑ ፡ እምያስተዋስቦሙ ፡ ወይከልእሙ ፡ በግፍዕ ፡ ከመ ፡ ኢያስተዋስብዎሙ ፡ ወኢይሁብዎሙ ፡ ትልወተ ፡ ድልወ ፡ ለሊሆሙንቱ ፡ ከመ ፡ የአዝዝዎ ፡ አስተዋስቦ ፡ ወትልወተ ።



የተቀበለችውን ፡ ሁሉ ፡ ትመልስ ። የሰጣትን ፡ እጅ ፡ መንሻም ፡ እንደ ፡ ዐረቦኑ ፡ ትመልስ ።

፰፻፹፰ ወስ ፡ ፫ ። እጅ ፡ መንሻ ፡ ግን ፡ ለማጨት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለማጋባት ፡ አይደለም ። በሠርግ ፡ ቀን ፡ የሚሆን ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ አለና ። በቤቷ ፡ ያለች ፡ ሴት ፡ ብትሆን ፡ እጅ ፡ መንሻው ፡ ለእርሷ ፡ ይሆናል ። ከሩቅ ፡ መጥቶ ፡ ያጫት ፡ ዕርሙኛው ፡ ናትና ። በሰው ፡ ቤት ፡ ያለችም ፡ ብትሆን ፡ እጅ ፡ መንሻዋ ፡ ለሴትዮዋ ፡ ትሆናለች ። የሰውየው ፡ ባለዕዳዎች ፡ ለዕርሙኛው ፡ ከሰጣት ፡ እጅ ፡ መንሻና ፡ ገንዘብ ፡ ምንምን ፡ አይውሰዱ ።

፰፻፹፱ ፬ ። ሴትም ፡ ማጫዋን ፡ ለመውሰድ ፡ ከባሏ ፡ ባለዕዳዎች ፡ በፊት ፡ ትቅደም ። ከሠርግ ፡ በፊት ስለሆነው ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ግን ፡ ከፊተኞች ፡ ባለዕዳዎች ፡ አትቅደም ።

፰፻፺ ፬ኛ ፡ ምዕራፍ ። ቢጋብቻ ፡ ጊዜ ፡ አባት ፡ ከልጁ ፡ ጋራ ፡ ስለሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ይናገራል ። ከሥልጣኑ ፡ በታች ፡ ስላለው ፡ እንደሚቀበል ፡ ገጸር ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ ይስጥ ። ወስ ፡ ፫ ፡ አባት ፡ ልጁን ፡ ከሥልጣኑ ፡ በታች ፡ ሳለ ፡ ልጁ ፡ በንጽሕና ፡ ቢኖር ፡ ለማጋባት ፡ ማስገደድ ፡ አይገባውም ። በሥራው ፡ ነዘንላል ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ትእዛዙን ፡ እንቢ ፡ ሊል ፡ አይገባውም ።

፰፻፺፩ ፭፫ ። አባት ፡ ሴት ፡ ልጁን ፡ ወይም ፡ የወንድ ፡ ልጁን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ የሴት ፡ ልጁን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ሊያጋባ ፡ (ሊድር) ፡ ቢወድ ፡ የተቻለውን ፡ ያህል ፡ ትሎቷን ፡ ቢሰጥ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከፉ ፡ ሥራን ፡ ወድዳ ፡ እንቢ ፡ ብትል ፡ ከርስቱ ፡ ትነቀል ።

፰፻፺፪ ፩ ። ልጆችም ፡ ትሎት ፡ በመስጠትና ፡ ከሠርግ ፡ በፊት ፡ የወሰዱትን ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ በመክፈል ፡ ዕዳ ፡ ውስጥ ፡ ሊያገቧቸው ፡ ወላጆቻቸውን ፡ በማስተየም ፡ ጋብቻን ፡ ሊያፈርሱ ፡ አይገባቸውም ። ወላጆችም ፡ ትሎት ፡ በመስጠት ፡ ከሠርግ ፡ በፊት ፡ የሚሰጡትን ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ የሚሰጡ ፡ አባቶች ፡ በመሆናቸው ፡ በምንም ፡ ጭንት ፡ የጋብቻን ፡ ሥርዓት ፡ ሊያፈርሱ ፡ አይገባቸውም ።

፰፻፺፫ ከሥልጣኑ ፡ በታች ፡ ያሉትን ፡ ከማጋባት ፡ ይልቅ ፡ የሚከለክል ፡ እንዳያጋቧቸውም ፡ በግፍዕ ፡ የሚከለክላቸው ፡ ትሎትም ፡ የማይሰጣቸውን ፡ አጋዛ ፡ ትሎት ፡ ስጥ ፡ ብለው ፡ ያዘዙት ፡ ዘንድ ፡ ለዳኞች ፡ ይገባል ።

## አንቀጽ ፡ ፳፬ ።

፳፱ ፺፬ ወዘሰ ኀለፈት ፳ወ፩ቱ ዓመተ ሰበ ተሀከዩ ወላድያኒሃ ፡ እምአስተዋስቦታ ፡ ይደሉ ፡ ላቲ ፡ ከመ ፡ ትልእክ ፡ ኀበ ፡ ሊቃውንት ፡ ከመ ፡ የአዝዝዎሙ ፡ ለወላድያኒሃ ፡ ያስተዋስብዋ ፡ ወየሀቡ ፡ ትሎታ ፡ በአምጣነ ፡ ክሂሎቶሙ ። ወእመሰ ፡ ሥልጣን ፡ ላቲ ፡ ለርእሳ ፡ ወይከውን ፡ ዓመታቲሃ ፡ ፍጹመ ፡ ድልው ፡ ላቲ ፡ ከመ ፡ ትንሣእ ፡ ምተ ፡ በከመ ፡ ይደሉ ፡ ለሕግ ፡ ወለእመኒ ፡ ኮነ ፡ አቡሃ ፡ ይጸልእ ፡ ዘንተ ። ወከመዝ ፡ ውእቱ ፡ ፍትሑ ፡ ለወልድ ፡ እመ ፡ ኮነ ፡ ተባዕተ ፡ እው ፡ አንስተ ።

፳፱ ፺፭ ወለእመ ፡ ኢተመይጠ ፡ ሙቁሕ ፡ በመጠነ ፡ ፳ቱ ፡ ዓመት ፡ ይደልዎ ፡ ለወልድ ፡ ከመ ፡ ያውስብ ፡ ወለእመ ፡ ኢተአምረ ፡ መካነ ፡ አብ ፡ በዝንቱ ፡ ፲ቱ ፡ ዓመት ፡ እመ ፡ ኮነ ፡ ሕያወ ፡ ይደልዎሙ ፡ ለደቂቁ ፡ ከመ ፡ ያውስቡ ፡ ዘፈቀዱ ፡ በከመ ፡ ትእዛዘ ፡ ሕግ ። ወውሉደ ፡ ሙቁሕ ፡ ወንጉዲ ፡ ሶበ ፡ አውሰቡ ፡ እምቅድመ ፡ ፲ቱ ፡ ዓመት ፡ ወተዐውቀ ፡ ከመ ፡ አቡሆሙ ፡ ኢያሥምር ፡ በዝንቱ ፡ ዘመድ ፡ ኢይሤኒ ፡ አውስቦቶሙ ። ወእመ ፡ ኮነ ፡ አቡሆሙ ፡ ዘአልቦ ፡ ልብ ፡ እምንዕሶሙ ፡ የአክል ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ለባዌ ፡ ወእመ ፡ አኮሰ ፡ ይኩን ፡ በምክረ ፡ አዝማዲሃ ።

፳፱ ፺፮ ወሶበ ፡ ተገአዙ ፡ ምስለ ፡ አንተ ፡ ልህቀት ፡ ይኩን ፡ በሥምረተ ፡ መኰንን ፡ ወለእመ ፡ መከረ ፡ ውእቱ ፡ እመሂ ፡ ከመ ፡ ምክረ ፡ አዝማዲሃ ፡ ወዘለሊሃ ፡ ኅረየት ፡ ዕሩያነ ፡ ኮኑ ፡ በአምሳል ፡ ወበምግባር ፡ ይግበሩ ፡ ዘከመ ፡ ኅረየት ፡ ለሊሃ ። ወለእመ ፡ ተናፈቁ ፡ በአንተ ፡ አስተዋስቦታ ፡ ለድክትምት ፡ አንተ ፡ ኢየብጸሐት ፡ መጠነ ፡ አካል ፡ አዝማዲሃ ፡ ወዐቃብያኒሃ ፡ ይኩን ፡ በዘኅረየ ፡ መኰንን ፡ ወዘሂ ፡ ይሜግብ ፡ ንዋያ ፡ ለድክምት ፡ ባሕቲቱ ፡ አልቦቱ ፡ መባሕት ፡ ለአስተዋስቦታ ፡ ኢከመ ፡ ይክልእ ፡ ወኢ ፡ ከመ ፡ የሀብ ። ወእለሂ ፡ የኀዝኑ ፡ በአንተ፡ አቡሆሙ ፡ ወእምኒዎሙ ፡ እለ ፡ ኀለፉ ፡ ኢይክልእዎሙ ፡ እምተዋስቦ ፡ በጊዜ ፡ ኀዘኖሙ ።

፳፱ ፺፯ ምዕራፍ ፡ ኃምስ ፡ በአንተ ፡ ውሳኔ ፡ አውስቦ ፡ ወግብረ ተሁ ፡ ወውእቱ ፡ ይትከፈል ፡ ኀበ ፡ ፰ቱ አክፋል ። ክፍል ፡ ቀዳማዊ ፡ በአንተ ፡ ውሳኔ ፡ ዘአውስቦ ፡ ወዝንቱ ፡ ተሰናእዎ ፡ ብእሲ ፡ ወብእሲት ፡ ውእቱ ፡ ተሠናእዎቶ ፡ ክሡተ ፡ በስምዕ፡

## ስለ ፡ ጋብቻ ።

፳፱ ፺፬ ፳፭ ፡ ዓመት ፡ ያለፋት ፡ ልጅ ፡ ወላጆቿ ፡ እርሷን ፡ ከማጋባት ፡ ቸል ፡ ቢሉ ፡ እንደአቅማቸው ፡ ትሎት ፡ ሰጥተው ፡ እንዲያጋቧት ፡ ወላጆቿን ፡ ያዝዙቸው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ዳኞች ፡ ልትልክ ፡ ለእርሷ ፡ ይገባታል ። ዘመኗ ፡ ብዙ ፡ ሆኖ፡ ለራሷ ፡ ሥልጣን ፡ ያላት ፡ ብትሆን ፡ ግን ፡ አባቷ ፡ ይህንን ፡ የሚጠላ ፡ ቢሆንም ፡ በሕግ ፡ እንደሚገባው ፡ ባል ፡ ታገባ ፡ ዘንድ ፡ ለእርሷ ፡ ይገባታል ። ወንድ ፡ ቢሆን ፡ ሴትም ፡ ብትሆን፡ የልጅ ፡ ፍርዱ ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ።

፳፱ ፺፭ ለ፲ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ የታሠረ ፡ እስረኛ ፡ ባይፈታ ፡ ልጁ ፡ ሊያገባ ፡ ይገባዋል ። አባት ፡ ደኅናም ፡ ቢሆን ፡ በዚሁ ፡ በ፲ሩ ፡ ዓመት ፡ ያለበት ፡ ቦታ ፡ ካልታወቀ ፡ ልጆቹ ፡ ሕግ ፡ ስለሚያዝዝ ፡ የወደዱትን ፡ ሊያገቡ ፡ ይገባቸዋል ። የእስረኛና ፡ እሩቅ ፡ አገር ፡ የሄደ ፡ ሰው ፡ ልጆች፡ ከ፲ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ቢያገቡ ፡ አባታቸውም ፡ ይኸን ፡ ዝምድና ፡ እንደማይወድ ፡ ቢታወቅ ፡ ግቢያቸው ፡ ተስማሚ ፡ አይሆንም ። አባታቸው አእምሮ ፡ የሌለው ፡ ቢሆን ፡ ባለአእምሮ ፡ ከሆነ ፡ እያታቸው ፡ ይበቃል ። ይህ ፡ ባይሆን ፡ ግን ፡ በዘመዶቿ ፡ ምክር ፡ ይሁን ።

፳፱ ፺፮ ካደገችው ፡ ጋራ ፡ በተከራከሩ ፡ ጊዜ ፡ በዳኛ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሁን ። እርሱም ፡ ቢመክር ፡ እንደዘመዶቿም ፡ ምክር ፡ ቢሆን ፡ እርሷም ፡ የመረጠችው ፡ በመልክ ፡ በሥራ ፡ የተካከሉ ፡ ቢሆኑ ፡ እርሷ ፡ እንደመረጠችው ፡ ያድርጉ ። አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰችውን ፡ ደኃ ፡ አደግ ፡ ልጅ ፡ ስለማጋባት ፡ (ስለመዳር) ፡ ዘመዶቿና ፡ ሞግዚቶቿ ፡ ቢለያዩ ፡ ዳኛ ፡ በመረጠው ፡ ይሁን ። የድኃ ፡ አደጊቱን ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠብቅ ፡ ሰው ፡ ብቻውን ፡ ሊያጋባት ፡ ወይም ፡ ሊከለክላት ፡ ወይም ፡ ሊሰጣት ፡ ሥልጣን ፡ የለውም ። ስለሞቱ ፡ አባታቸውና ፡ እያታቸው ፡ የሚያዝኑትን ፡ በሚያዝኑበት ፡ ወራት ፡ ከጋብቻ ፡ አይከልክሏቸው ።

፳፱ ፺፯ አምስተኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ስለጋብቻ ፡ ውሳኔና ፡ ስለ ፡ ሥራዎቹም ፡ ይናገራል ። ይኸውም ፡ ከ፰ ፡ ወገን ፡ ይከፈላል ። መጀመሪያው ፡ ክፍል፡ ስለጋብቻ ፡ ውሳኔ ፡ ይናገራል ። ይኸውም ፡ በእውነተኛ ፡ ምስክር ፡ አንድ ፡ ለማድረግ ፡ በሚ

ጽዱቅ ፡ ወበጸሎተ ፡ ካህናት ፡ ለአስተፃምሮ ፡
ወለሕይወት ፡ በስንእዊ ፡ ወለአጥርዮ ፡ ጥሪታት
በዘይትረድኡ ፡ በእንተ ፡ ረኪበ ፡ መፍቅዳቲ
ሆሙ ፡ ወለወሊደ ፡ ዘርእ ፡ ዘይተርፍ ፡ ኅቡረ ፡
እምድኅሬሆሙ ።

፰፻፺፫ ዳግም ፡ ዘናቅድም ፡ ንገረ ፡ በእንተ ፡ ተዋስቦ ።
ጠስ ፡ ፬ቱ ፡ ኢይኩን ፡ ሥርዓተ ፡ ተዋስቦ ፡ ዘያ
ስተዋስብዎሙ ፡ ዘእንበለ ፡ በተማምሮቶሙ ፡
ለክልኤሆሙ ፡ ወበሥምረተ ፡ ሐፃንያቲሆሙ ።
ወእለሂ ፡ ይትዋሰቡ ፡ ይኩኑ ፡ ብጹሓነ ፡ አም
ጣነ ፡ ብእሲ ፡ ወብእሲት ፡ ለብእሲኒ ፡ ዘኮነ ፡
ሎቱ ፡ ፳ ፡ ዓመታቲሁ ፡ ወለብእሲትኒ ፡ ዘኮና ፡
፲ወ፪ቱ ፡ ዓመት ። ወእንተሰ ፡ ተወሰበት ፡ በካ
ልእ ፡ እምነ ፡ ዝንቱ ፡ ኢትከውን ፡ ብእሲተ ፡
ዘበሕግ ፡ ለእመ ፡ ኢተወከፈት ፡ ትድምርተ ፡
ብእሲ ። ወእለሰ ፡ ያስተዋስብዎሙ ፡ ይለወ ፡
ሎሙ ፡ መጠነ ፡ ዝንቱ ፡ በዘይከውን ፡ ተዋስቦ ፡
ሕጋዊ ፡ ዘድልው ፡ ለብእሲ ፡ ወብእሲት ፡ ወኢ
ይግበሩ ፡ ሎሙ ፡ ተክሊለ ፡ ምንተኒ ፡ በኅቡእ ፡
እንበለ ፡ ይትጋብኡ ፡ ብዙኃን ፡ አላ ፡ ይግበሩ ፡
በቅድመ ፡ ብዙኃን ።

፰፻፺፬ መጽ ፡ ፩ዱ ፡ ወማእሠረ ፡ ተዋስቦስ ፡ ኢይከውን
ወኢይትፌጸም ፡ ዘእንበለ ፡ በሀልዎተ ፡ ካህ
ናት ፡ ወጸሎት ፡ ዘላዕሌሆሙ ፡ ወይመጥው
ዎሙ ፡ ቍርባነ ፡ ቅዱስ ፡ በጊዜ ፡ ተክሊል ፡
ዘቦቱ ፡ ይትዋሐዱ ፡ ክልኤሆሙ ፡ ወይከውኑ ፡
፩ደ ፡ ሥጋ ፡ በከመ ፡ ነገረ ፡ እግዚእነ ፡ ሎቱ ፡
ስብሐት ። ወዘእንበለ ፡ ዝንቱሰ ፡ ኢይትኀለቍ ፡
ሎሙ ፡ እውስቦ ፡ እስመ ፡ ጸሎት ፡ ይእቲ ፡ እንተ
ትፌትሕ ፡ እንስተ ፡ ለእደ ፡ ወእደ ፡ ለአንስት ።

፱፻ ክፍል ፡ ሣልስ ፡ በእንተ ፡ ግጻተ ፡ ተዋስቦ ፡ ወዘ
ይትልዎ ፡ ወውእቱ ፡ ፲ወ፩ዱ ፡ ግጽ ። ግጽ ፡ ቀዳ
ማዊ ፡ ይትከፈል ፡ ኀበ ፡ ኃምስቱ ፡ ክፍል ።
ክፍል ፡ ቀዳሚ ፡ እውስቦ ፡ ቀዳማዊ ፡ ወናሁ ፡
ቀደመ ፡ ነገር ፡ በእንቲአሁ ፡ ውስተ ፡ ግጽ ፡
ቀዳማዊ ።

፱፻፩ ወዳግምኒ ፡ እውስቦ ፡ ዳግማዊ ። መጽ ፡ ፯ቱ ፡
ወለእደውሰ ፡ ይደልዎሙ ፡ እውስቦ ፡ ዳግማዊ ፡
ዘኢክሉል ። ወለእመ ፡ ኮኑ ፡ ሎሙ ፡ ውሉድ ፡
ሕፃናት ፡ ይደልዎሙ ፡ ከመ ፡ ይዕቀቡ ፡ ርስ



ሆን ፡ በካህናት ፡ ጸሎት ፡ በስምምነት ፡ ለመ
ኖር ፡ ፍላጎታቸውን ፡ ስለማግኘት ፡ በሚረ
ዳዱ ፡ ገንዘብ ፡ ሀብትን ፡ ለማግኘት ፡ ከእነር
ሱም ፡ በኋላ ፡ የሚተካ ፡ ልጅ ፡ በአንድነት ፡
ለመውለድ ፡ በግልጥ ፡ ስምምነት ፡ የባልና ፡
ሚስት ፡ መስማማት ፡ ነው ።

፰፻፺፫ ዳግመኛ ፡ መናገርን ፡ የምናስቀድም ፡ ስለ ፡
ጋብቻ ፡ ነው ። ጠስ ፡ ፬ ። የሚያጋቧቸው ፡ የጋ
ብቻ ፡ ሥርዓት ፡ ያለሁለቱ ፡ መፈቃቀድ ፡ ያላ
ሳዳጊዎቻቸውም ፡ ፈቃድ ፡ አይሁን ። የሚጋ
ቡትም ፡ የሴትና ፡ የወንድ ፡ አካለ ፡ መጠን ፡
ያደረሱ ፡ ይሁኑ ። ወንዱ ፡ ኻያ ፡ ዓመት ፡ የሆ
ነው ፡ ሴቷም ፡ ፲፪ ፡ ዓመት ፡ የሆናት ፡ ይሁኑ ።
ከዚህ ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ የገባች ፡ ሴት ፡ የባሏን ፡
መገናኘት ፡ ካልተቀበለች ፡ የሕግ ፡ ሚስት ፡ አት
ሆንም ። ሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ ለወድና ፡ ለሴት ፡
የሚገባ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ለሚያጋቧቸው ፡
ልጆች ፡ ይህ ፡ የዘመን ፡ ልክ ፡ ተገባቸው ።
ብዙዎች ፡ ሳይሰበሰቡ ፡ በስውር ፡ ምንም ፡ ተክ
ሊል ፡ አያድርጉላቸው ። በብዙዎች ፡ ፊት ፡ ያድ
ርጉ ፡ እንጂ ።

፰፻፺፬ መጽ ፡ ፩ ። የጋብቻ ፡ አንድነት ፡ ግን ፡ በካህ
ናት ፡ መኖር ፡ በላያቸው ፡ በሚጸልዩት ፡ ጸሎት፡
ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አይሆንም ፡ አይፈጸምም ።
ሁለቱ ፡ አንድ ፡ በሚሆኑበት ፡ በተክሊልም ፡
ጊዜ ፡ ቅዱስ ፡ ቍርባንን ፡ ያቀብሏቸው ። ምስ
ጋና ፡ ይግባውና ፡ ጌታችን ፡ እንደተናገረ ፡ ፩ ፡
አካል ፡ ይሆናሉ ። (ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፭) ። ያለዚህ ፡
ግን ፡ ጋብቻ ፡ ተብሎ ፡ አይቆጠርላቸውም ።
ወንዶችን ፡ ከሴቶች ፡ ሴቶችንም ፡ ከወንዶች ፡
፩ ፡ የምታደርግ ፡ ጸሎት ፡ ናትና ።

፱፻ ፫ኛ ፡ ክፍል ። ስለ ጋብቻና ፡ ስለሚከተለው ፡
ግብረት ፡ ይናገራል ። ይኸውም ፡ ፲፩ ፡ ክፍል ፡
ነው ። መጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ ከ፭ ፡ ይከፈላል ።
መጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ መጀመሪያውን ፡
ጋብቻ ፡ ይናገራል ። እነሆ ፡ ስለእርሱም ፡ በመ
ጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ አስቀድሞ ፡ ተነግሯል ።
ሁለተኛውም ፡ ሁለተኛውን ፡ ጋብቻ ፡ ይናገ
ራል ።

፱፻፩ መጽ ፡ ፯ ። ለወንዶች ፡ ግን ፡ ተክሊል ፡ የማያደ
ርስበት ፡ ሁለተኛ ፡ ጋብቻ ፡ ይገባቸዋል ። ለእነ
ርሱም ፡ ሕፃናት ፡ ልጆች ፡ ቢኖሯቸው ፡ ከእናታ
ቸው ፡ የተካፈሉትን ፡ ርስታቸውን ፡ ይጠብቁ ፡

ቀሙ ፡ ዘተከፈሉ ፡ እምርስተ ፡ ወላዲቶሙ ፡ እስመ ፡ ኢይደሉ ፡ ለሙ ፡ ኀደጎተ ፡ ውሉደሙ ።

፱፻፪ ጠስ ፡ ፳ቱ ፡ ወለእመ ፡ ኮኑ ፡ እደው ፡ ካህናተ ፡ ይደቱ ፡ እመዓርጊሆሙ ፡ ወእምድኅረሁስ ፡ ለእመ ፡ ደገሙ ፡ ይከውኑ ፡ ርኩሳነ ።

፱፻፫ ዘኒቅያ ፡ ፲ወ፱ቱ ፡ ወእለሰ ፡ ያወስቡ ፡ ዳግመ ፡ እምድኅረ ፡ ብዕሲት ፡ ውእቱኬ ፡ ዐሊዎተ ፡ ሕግ ፡ አኮ ፡ በእንተ ፡ ተደምሮ ፡ አላ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ሐስወ ፡ ላዕለ ፡ ፈጣሪሁ ።

፱፻፬ በስ ፡ ፹ወ፱ቱ ፡ ዕቤርስ ፡ እምድኅረ ፡ ኮና ፡ ፳ ፡ ዓመት ፡ ወተመይጠት ፡ ዳግመ ፡ ለተወስቦ ፡ ትሰደድ ፡ እስመ ፡ ይእቲ ፡ ኮነት ፡ ዘማዊተ ።

፱፻፭ ዘቆርንቶስ ፡ ፳ቱ ፡ ወብእሲትኒ ፡ እምጣነ ፡ ሀሎ ሕያወ ፡ ምታ ፡ እሡርት ፡ ይእቲ ፡ በሕግ ። ወእመሰ ፡ ሞተ ፡ ምታ ፡ ትግዕዘ ፡ ወይደሉ ፡ ትትወሰብ ፡ ለዘፈቀደት ፡ እምእመናን ፡ እግዚአብሔር ። ወብፅዕት ፡ ይእቲ ፡ ለእመ ፡ ጸንዐት፡ በምክርየ ፡ ወእመሰ ፡ ስእነት ፡ ተዓግሦ ፡ ትትወሰብ ።

፱፻፮ በስ ፡ ወለእመ ፡ ኮኑ ፡ ዘይትዋሰቡ ፡ መዓስባነ ፡ ኢይግበሩ ፡ ሎሙ ፡ በረከተ ፡ ተክሊል ። እስመ ፡ ዝንቱ ፡ በረከት ፡ ይደሉ ፡ ለብእሲ ፡ ድንግል ፡ ወለብእሲት ፡ ድንግልት ፡ በጊዜ ፡ ተዋስቦ ። ወለእመ ፡ ደገሙስ ፡ ይደልዎሙ ፡ ጸሎተ ፡ ካህን ፡ ዘእስተሥርዮ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ፩ዱ ፡ እምተዋሳብያን ፡ ድንግለ ፡ ለይትባረክ ፡ ባሕቲቱ ፡ ወዝቲ ፡ ሕግ ፡ ለእደው ፡ ወለአንስት ፡ ኀቡረ ።

፱፻፯ መጅ ፡ ፯ቱ ፡ ወዘተወሰበት ፡ እምኔሆን ፡ ወኮኑ ፡ ላቲ ፡ ውሉድ ፡ ይደሉ ፡ ላቲ ፡ ከመ ፡ ታስተባውሖሙ ፡ ለውሉዳ ፡ እምቅድመ ፡ ትትወሰብ ፡ ወትትፋለጥ ፡ ንዋየ ፡ እምዘ ፡ ባቲ ፡ ወተሀቦሙ ፡ ለውሉዳ ።

፱፻፰ ጠስ ፡ ፬ቱ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ መዋዕሊሃ ፡ መጠነ ፡ ፳ወ፭ቱ ፡ ዓመት ፡ ላቲ ፡ ሥልጣን ፡ በርእሳ ፡ በከመ ፡ ፈቀደት ፡ ትትወሰብ ፡ ዳግመ ፡ በምክረ ፡ አቡሃ ። ወለእመሰ ፡ ሞተ ፡ አቡሃ ፡ ይኩን፡ በምክረ ፡ እዝማዲሃ ። ወእመሰ ፡ ተኀጥኡ ፡ አዝማዲሃ ፡ ይኅድስዎሙ ፡ ፈድፋደ ፡ ኀበ ፡ ሊቀ ፡ ይብጽሑ ፡ ፈኃርያን ፡ ከመ ፡ ይሥርዮሙ ፡ በዘይደሉ ። ወለእመኒ ፡ ኮነ ፡ ፈኃሪ ፡ ዘየኀርያ ስብእ ፡ ዘእሃ ፡ ወዘኀረዮቶ ፡ ለሊሃ ፡ ወለት ፡ ዕሩ



ዘንድ ፡ ይገባቸዋል ። ልጆቻቸውን ፡ መተው ፡ አይገባቸውምና ።

፱፻፪ ጠስ ፡ ፳ ። ሁለተኛ ፡ የሚጋቡት ፡ ወንዶች ፡ ካህናት ፡ ቢሆኑ ፡ ከሹመታቸው ፡ ይሻሩ ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ቢደግሙ ፡ የረከሱ ፡ ይሆናሉ ።

፱፻፫ ኒቅያ ፡ ፲፱ ። ከብዕሳት ፡ በኋላ ፡ ዳግመኛ ፡ የሚያገቡ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ማፍረስ ፡ ነው ። ስለ መገናኘት ፡ አይደለም ። በፈጣሪው ፡ ላይ ፡ ሐሰት ፡ ስለተናገረ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፱፻፬ በስ ፡ ፹፱ ። እሮጊት ፡ ግን ፡ ፳ ፡ ዓመት ፡ ከሆናት ፡ በኋላ ፡ ተመልሳ ፡ ሁለተኛ ፡ ብታገባ ፡ ትለይ ። እርሷ ፡ አመንዝራ ፡ ሁናለችና ።

፱፻፭ ቆሮ ፡ ፳ ። ሴት ፡ ባሏ ፡ በሕይወት ፡ ሳለ ፡ በሕግ ፡ የታሠረች ፡ ናት ። ባሏ ፡ ቢሞት ፡ ግን ፡ ነፃ ፡ ናት ። እግዚአብሔርን ፡ ከሚያምኑ ፡ ወገን ፡ የወደደችውን ፡ ልታገባ ፡ ይገባታል ። በምክሬ ፡ ብትፀና ፡ ብፅዕት ፡ ናት ። መታገሥ ፡ ቢሳናት ፡ ግን ፡ ታግባ ። (፩ኛ ፡ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፹፱) ።

፱፻፮ የሚጋቡት ፡ ፈቶች ፡ ቢሆኑ ፡ ተክሊል ፡ አያድርጉላቸው ። ይህ ፡ በረከት ፡ (ተክሊል) ፡ በጋብቻ ጊዜ ፡ ለድንግል ፡ ወንድና ፡ ለድንግል ፡ ሴት ፡ ይገባልና ። ቢደግሙ ፡ ግን ፡ ማስተሥርያ ፡ የሚሆን ፡ የካህን ፡ ጸሎት ፡ ይገባቸዋል ። ከሚጋቡት አንዱ ፡ ድንግል ፡ ቢሆን ፡ ብቻውን ፡ ይባረክ። ይህች ፡ ሕግ ፡ ለወንዶችም ፡ ለሴቶችም ፡ ባንድነት ፡ ትገባለች ።

፱፻፯ መጅ ፡ ፯ ። ከእነዚህ ፡ ወገን ፡ ያገባችው ፡ ልጆች ቢኖሯት ፡ ከማግባቷ ፡ አስቀድማ ፡ ካላት ፡ ገንዘብ ፡ ለይታ ፡ ለልጆቿ ፡ ሰጥታ ፡ ልጆቿን ፡ ልታስናብት ፡ ይገባታል ።

፱፻፰ ጠስ ፡ ፬ ። ዕድሜዋ ፡ ፳፭ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ቢሆን ፡ እንደ ፡ ወደደች ፡ ልታገባ ፡ በራሷ ፡ ሥልጣን ፡ አላት ። ዳግመኛም ፡ በአባቷ ፡ ምክር፡ አባቷ ፡ ቢሞት ፡ ግን ፡ በዘመዶቿ ፡ ምክር ፡ ይሁን ። ዘመዶቿ ፡ ቢጣሉ ፡ ግን ፡ በሚገባ ፡ ይጠሰንላቸው ፡ ዘንድ ፡ አጭታዎች ፡ ይልቁንም ፡ ወይ ፡ ዳኛ ፡ ቢሄዱ ፡ ይሻላቸዋል ። ቢተ ፡ ሰቦቿ፡ የመረጡት ፡ ዕጮኛና ፡ እርሷ ፡ ልጅቱ ፡ የመረጠችው ፡ ዕጮኛ ፡ በወገንም ፡ በሞያም ፡ ትክክ

ያን ፡ ውስተ ፡ ዘመድ ፡ ወግብር ፡ ይኩን ፡ ምክረ ፡ ብእሲት ፡ ዘይትገበር ፡ ላዕሌሁ ።

፱፻፱ ወግልስኒ ፡ በእንተ ፡ አውስቦ ፡ ግልስ ፡ ድስቅ ፡ ፲ወ፱-ቱ ፡ አውስቦሰ ፡ ግልሳዊ ፡ ውእቱ ፡ ትእምርተ ፡ ስሕተት ፡ ወለእመ ፡ ከሀለ ፡ የአኀዝ ፡ ርእሶ ። ዘ፲ወ፩ዱ ፡ ወይእቲ ፡ ንዋይ ፡ ርስሕት ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

፱፻፲ ወራብዕ ፡ ድስቅ ፡ ፲ወ፱-ቱ ፡ ወለእመ ፡ በዝንቱ ፡ አምግልስ ፡ ወውእቱ ፡ ትእምርተ ፡ ዝሙት ፡ ከሡት ። ጠስ ፡ ፬-ቱ ፡ ወለእመ ፡ ተኀበለ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ላዕለ ፡ አውስቦ ፡ ራብዕ ፡ ዘኢኮነ ፡ አውስቦ ፡ ውእቱ ፡ ኢይትኆለቍ ፡ ውስተ ፡ ሕገ ፡ ተዋስቦ ፡ ዝንቱሰ ። ወኢይደሉ ፡ ይኩኑ ፡ እለ ፡ ተወልዱ ፡ እምኔሁ ፡ ድልዋነ ፡ ወዕጡቃነ ፡ ወይትወደዩ ፡ ውስተ ፡ ክህነት ፡ ይነሳውያን ፡ በርኩስ ፡ ዝሙት ፡ ወይፍልጥዎሙ ፡ ለለ ፩ዱ ፡ እምኒልኡ ።

፱፻፲፩ ወኅምስሂ ፡ ዘኒቅያ ፡ ፳ወ፪-ቱ ፡ ወኢያስተጋብእ ፡ ኅቡሬ ፡ ብእሲ ፡ ፪-ተ ፡ አንስተ ፡ በምክንያተ ፡ ተድላ ። ወበዊእስ ፡ ውስተ ፡ ብዝኁ ፡ አውስቦ ፡ በእንተ ፡ ፍትወት ፡ ውእቱ ፡ ወአኮ ፡ ለዘርአ ፡ ዘእዘዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቦቱ ። ወለእመሰ ፡ ገብረ ፡ ዘንተ ፡ ይትከላእ ፡ እምንግሥ ፡ ቍርባን ፡ ወእምበዊአ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወኢይባእ ፡ ውስተ ፡ ጉባኤ ፡ እስከ ፡ ይፈልጣ ፡ ለዳግሚት ፡ ወይንብር ፡ ምስለ ፡ ቀዳማዊት ። ዘ፸ ፡ ወለእመ ፡ አስተጋብኦን ፡ ለክልኤሆን ፡ አው ፡ ፈለጦን ፡ ለለአሐቲ ፡ እምኔሆን ፡ በበአብያቲሆን ፡ አው ፡ አንበረ ፡ ብእሲተ ፡ ወዕቅብተ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ካህነ ፡ ይሥዐር ፡ እምክህነቱ ፡ ወእመኒ ፡ ሕዝባዊ ፡ ይከልእዎ ፡ እምትድምርተ ፡ ሕዝብ ። ዘሮሜ ፡ ፱-ቱ ፡ ወብእሲትኒ ፡ ለእመ ፡ ቀርበት ፡ እንዘ ፡ ሕያው ፡ ምታ ፡ ብእሲ ፡ ካልእ ፡ ኮነት ፡ ዘማዊተ ፡ ወተዓዳዊተ ፡ ሕግ ።

፱፻፲፪ ገጽ ፡ ካልእ ፡ ዘኒቅያ ፡ ፶ወ፪-ቱ ፡ ድስቅ ፡ ፴ወ፩ዱ ፡ ወብእሲ ፡ ምእመን ፡ ለእመ ፡ አውሰበ ፡ ኢአማኒተ ፡ ይኤዝዝ ፡ በዊአታ ፡ ውስተ ፡ ሃይማኖት ። ወአንስትሰ ፡ ምእመናት ፡ ኢይትወሰባ ፡ ለእደው ፡ እለ ፡ ውፁአን ፡ እምሃይማኖት ፡ ከመ ፡ ኢይሚጥዎን ፡ ኀበ ፡ ሃይማኖቶሙ ፡ ወኢያውፅእዎን ፡ እምሃይማኖት ።

፱፻፲፫ ዘኒቅያ ፡ ፸ወ፱-ቱ ፡ ወብእሲት ፡ ማእምንት ፡ ለእመ ፡ ተወሰበት ፡ ለብእሲ ፡ ኢአማኒ ፡ ትስ



ል ፡ ቢሆኑ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ የሴቲቱ ፡ ፈቃድ ፡ ይሁን ።

፱፻፱ ፫ኛው ፡ ስለ፫ኛ ፡ ግቢ ፡ ይናገራል ። ድስቅ ፡ ፲፱ ። ፫ኛ ፡ ጋብቻ ፡ ግን ፡ የስሕተት ፡ ምልክት ፡ ነው ። ከቻለ ፡ ራሱን ፡ ይያዝ ። ፲፩ ። ይህችም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ የጕሰቈለች ፡ (የረከሰች) ፡ ዕቃ ፡ ናት ።

፱፻፲ ፬ኛው ፡ ድስቅ ፡ ፲፱ ። ከሦስት ፡ ቢበዛ ፡ የተገለጸ ፡ የዝሙት ፡ ምልክት ፡ ነው ። ጠስ ፡ ፬ ። ጋብቻ ፡ ያይደለ ፡ ፬ኛ ፡ ጋብቻን ፡ ሊያደርግ ፡ ቢደፋፈር ፡ ይህስ ፡ ከጋብቻ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ አይቆጠርም ። ከእነርሱ ፡ የተወለዱት ፡ የታወቁ ፡ የተገቡ ፡ ሊሆኑ ፡ አይገባም ። በርኩስ ፡ ዝሙት ፡ ወደ፡ንጢአተኞች ፡ ቅጣት ፡ ይጨመሩ ። እያንዳንዳቸውን ፡ ከሁለተኛው ፡ ይለዩዋቸው ።

፱፻፲፩ ፭ኛው ፡ ኒቅያ ፡ ፳፪ ። ሰው ፡ በምቾት ፡ ምክንያት ፡ ሁለት ፡ ሴቶችን ፡ አይሰብስብ ፡ (አያግባ) ፡ ወደ ፡ ጋብቻ ፡ ብዛት ፡ መግባት ፡ ግን ፡ ስለ ፍቲው ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ በእርሱ ፡ ላዘዘው ፡ ዘርስ ፡ አይደለም ። ይህን ፡ ቢያደርግ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከመግባት ፡ ቍርባንንም ፡ ከመቀበል ፡ ይከልከል ። ሁለተኛ ይቱን ፡ ፈትቶ ፡ ከመጀመሪያዋ ፡ ጋራ ፡ እስኪኖር ፡ ድረስ ፡ ከአንድነት ፡ ውስጥ ፡ አይግባ ። ፸ ፡ ሁለቱን ፡ አንድላይ ፡ ቢያኖራቸው ፡ ወይም ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በእየቤታቸው ፡ ቢለያቸው ፡ ወይም ፡ ዕቁባት ፡ ሴት ፡ ቢያኖር ፡ ካህን ፡ ቢሆን ፡ ከክህነቱ ፡ ይሻር ፡ ሕዝባዊ ፡ ቢሆን ፡ ከምእመናን ፡ አንድነት ፡ ይከልከሉት ። ሮሜ ፡ ፱ ። ሴት ፡ ባሏ ፡ በሕይወት ፡ ሳለ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ብታገባ ፡ ሴሰኛ ፡ ሕግ ፡ አፍራሽም ፡ ሆነች ። (ሮሜ ፡ ፯ ፡ ፫) ።

፱፻፲፪ ሁለተኛ ፡ ክፍል ። ኒቅያ ፡ ፶፯ ፡ ድስቅ ፡ ፴፩ ። አማኒ ፡ ወንድ ፡ ያላመነችውን ፡ ቢያገባ ፡ ወደ ፡ ሃይማኖት ፡ መግባቷን ፡ ያዝዛል ። አማኞች ፡ ሴቶች ፡ ግን ፡ ከሃይማኖት ፡ ለወጡት ፡ ወንዶች፡ ሚስቶች ፡ አይሁኑ ። ከሃይማኖት ፡ አስወጥተው ፡ ወደሃይማኖታቸው ፡ እንዳይመልሷቸው ።

፱፻፲፫ ኒቅያ ፡ ፸፱ ። ያመነች ፡ ሴት ፡ ያላመነ ፡ ወንድ ፡ ብታገባ ፡ ከምእመናን ፡ ትለይ ። ከሐዲ ፡ ከክህ

አንቀጽ ፡ ፳፬ ።

ደድ ፡ እምጉባኤ ። ወለእመ ፡ ነስሐት ፡ ወተከል
እት ፡ እምኔሁ ፡ ይትወከፍዋ ፡ በከመ ፡ ይትመ
የጥ ፡ ከሉሄ ፡ እምከሕደቱ ። ወእምድኅረ ፡ ነጽ
ሐት ፡ ያደልዋ ፡ ተደምሮ ፡ ምስለ ፡ ምእመናን ፡
ወየሀብዋ ፡ ቍርባነ ።

፱፻፲፬ ዘ፸ወ፫ቱ ፡ ወብእሲ ፡ ምእመን ፡ ለእመ ፡ አስተ
ዋሰበ ፡ ወለቶ ፡ አው ፡ እኅቶ ፡ ለዘኢየአምን ፡
ዘእንበለ ፡ ፈቃዶን ፡ ወኢየአምሮቶን ፡ ከመ ፡
ኢአማኒ ፡ ውእቱ ፡ ይሰደድ ፡ እምጉባኤ ፡ ወይ
ትከላእ ፡ እምተደምሮ ፡ ምእመናን ፡ ወለይእ
ቲሰ ፡ ኢይሰድድዋ ። ወእመሰ ፡ ነስሐ ፡ ወፈ
ለጣ ፡ እምኔሁ ፡ የሀብዎ ፡ ንስሓ ፡ በአምጣነ ፡
ከሂሎቱ ዘይከል ፡ በዋሮቶ ፡ ወእምዝ ፡ ይሥ
ረዩ ፡ ሎቱ ።

፱፻፲፭ ዘቀርንቶስ ፡ ፯ቱ ፡ ወለእመቦ ፡ እኍ ፡ ዘቦቱ ፡
ብእሲት ፡ ዘኢተአምን ፡ ወፈቀደት ፡ ትንበር ፡
ምስሌሁ ፡ ኢይኅድጋ ። ወብእሲትኒ ፡ ማእም
ንት ፡ እመ ፡ ባቲ ፡ ምት ፡ ዘኢየአምን ፡ ወይፈ
ቅድ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ይንበር ፡ ምስሌሃ ፡ ኢትት
ፈለጦ ፡ ለምታ ። እስመ ፡ ብእሲ ፡ ዘኢየአምን ፡
ይትቄደስ ፡ በብእሲት ፡ ማእምንት ። ወከማሁ ፡
ብእሲትኒ ፡ ዘኢተአምን ፡ ትትቄደስ ፡ በብእሲ ፡
ምእመን ፡ ወለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ዘኢየአምን ፡ ተፈ
ልጦ ፡ ይትፈለጡ ።

፱፻፲፮ ገጽ ፡ ኀልስ ፡ በአንተ ፡ ኍነ ፡ መዋዕል ፡ ዘኢይ
ደልዎ ፡ ለ፩ዱሂ ፡ እምእለ ፡ አውሰቡ ፡ ከመ ፡
ያውስቡ ፡ ባቲ ፡ እምድኅረ ፡ ሞተ ፡ ፩ዱ ፡ እም
እሉ ፡ ወውእቱ ፡ ፱ቱ ፡ ቃላት ፡ ፩ዱ ፡ እምኔ
ሆሙ ፡ መ፳ ፡ ፯ቱ ፡ ጠስ ፡ ፲ ፡ ወኢይደልዎ ፡
ከመ ፡ ያውስብ ፡ ዘእንበለ ፡ ይኅልፍ ፡ ፩ዱ ፡
ዓመት ፡ እሞተ ፡ ብእሲቱ ። ወእመሰ ፡ አውሰበ፡
እምቅድመ ፡ ፍጻሜ ፡ ዓመት ፡ ይትከላእ ፡ እም
ኵሉ ፡ ንዋይ ፡ ዘይደልዎ ፡ ዘኅደገቶ ፡ ብእሲቱ ።
መክ ፡ ፳ወ፯ቱ ፡ ፸ወ፳ቱ ፡ ወእመኒ ፡ ብእሲት ፡
አውሰበት ፡ ብእሲ ፡ እምቅድመ ፡ ይትፈጸም ፡
፲ቱ ፡ አውራኅ ፡ እምአመ ፡ ሞተ ፡ ምታ ፡ ኢት
ረስ ፡ እምንዋዩ ፡ ምንተኒ ፡ ወእምዘ ፡ እዘዘ ፡
ላቲ ፡ ኢየሀብዋ ። ወለእመ ፡ ጕለተ ፡ ላቲ ፡ ኢት
ሰድ ፡ ወኢያከብርዋ ፡ ከመ ፡ አንስት ፡ አማዓ
ዚያት ።

፱፻፲፯ ገጽ ፡ ራብዕ ፡ ጠስ ፡ ፳ቱ ፡ ወብእሲት ፡ ሶበ ፡
ጸንዐ ፡ እውስቦታ ፡ ወኮነ ፡ ምታ ፡ ጽኑስ ፡ በእንተ፡
ዘወሀበ ፡ ቀዲሙ ፡ እምአምኃ ፡ ወሕጻ ፡ ወእኑ

ስለ ፡ ጋብቻ ።

ደቱ ፡ እንደ ፡ እሚመለስ ፡ ብትመለስና ፡ ከእርሱ
ብትለይ ፡ ይቀበሏት ። ከነጻች ፡ በኋላ ፡ ከምእመ
ናን ፡ ልትገናኝ ፡ ይገባታል ። ቍርባንንም ፡
ያቀብሏት ።

፱፻፲፬ ፸፫ ። እማኒ ፡ ሰው ፡ ልጁን ፡ ወይም ፡ እኅቱን ፡
እማኝ ፡ እንዳይደለ ፡ ሳያውቁ ፡ ያለፈቃዳቸው ፡
ላላመነ ፡ ሰው ፡ ቢያጋባ ፡ ከጉባኤ ፡ ይለይ ።
ከምእመናን ፡ ጋራ ፡ ከመገናኘትም ፡ ይከልከል ።
እርሷን ፡ ግን ፡ አይለይዋት ። ተጸጽቶ ፡ ከእርሱ ፡
ቢለያት ፡ ግን ፡ እንደችሎቱ ፡ መጠን ፡ ሊሸከ
መው ፡ የሚችለውን ፡ ንስሐ ፡ ይስጡት ። ከዚህ
በኋላ ፡ ይቅር ፡ ይበሉት ።

፱፻፲፭ ቆሮ ፡ ፯ ። ያላመነች ፡ ሚስት ፡ ያለችው ፡ ወን
ድም ፡ ቢኖር ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ልትኖር ፡ ብት
ወድ ፡ አይፍታት ። ያመነች ፡ ሴትም ፡ ያላመነ ፡
ባል ፡ ቢኖራት ፡ እርሱም ፡ ከእርስዋ ፡ ጋራ ፡
ሊኖር ፡ ቢወድ ፡ ባሏን ፡ አትፍታው ፡ ያላመነ ፡
ወንድ ፡ ባመነች ፡ ሴት ፡ ይከብራልና ። እንደ
ዚኸውም ፡ ያላመነች ፡ ሴት ፡ ባመነ ፡ ወንድ ፡
ትከበራለች ። ያላመነው ፡ መለየትን ፡ ቢወድ ፡
ግን ፡ ይለያዩ ። (፩ኛ ፡ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፲፪ - ፲፭) ።

፱፻፲፮ ፫ኛው ፡ ክፍል ። ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ ከሞተ ፡
በኋላ ፡ ከተጋቡት ፡ ወገን ፡ ለአንዱስ ፡ እንኳ ፡
ሊያገቡበት ፡ ስለ ማይገባ ፡ ስለጊዜው ፡ ርዝ
መት ፡ ይናገራል ። ይኸውም ፡ ፱ ፡ ነገር ፡ ነው ።
ከእነርሱ ፡ ፩ ፡ መ፳ ፡ ፯ ። ጠስ ፡ ፲ ። ሚስቱ ፡
ከሞተችበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡
ካላለፈ ፡ በቀር ፡ ሊያገባ ፡ አይገባውም ።
ዓመቱ ፡ ሳይፈጸም ፡ ቢያገባ ፡ ግን ፡ ሚስቱ ፡ ከተ
ወችለት ፡ ሊወርሰው ፡ ከሚገባው ፡ ገንዘብ ፡
ሁሉ ፡ ይከልከል ። መክ ፡ ፳፯ ፡ ፸፳ ። ሴትም ፡
ባሏ ፡ ከሞተበት ፡ ጀምሮ ፡ አሥር ፡ ወር ፡ ሳይፈ
ጸም ፡ ባል ፡ ብታገባ ፡ ከገንዘቡ ፡ ምንም ፡ አት
ውረስ ። ከአዘዘላትም ፡ አይስጧት ። ቢጉልት
ላትም ፡ አትውሰድ ። እንደ ፡ እመቤቶችም ፡
ሴቶች ፡ አያክብሯት ።

፱፻፲፯ ፬ኛው ፡ ክፍል ፡ ጠስ ፡ ፳ ። የሴት ፡ ጋብቻዋ ፡
ቢጸና ፡ ከማጫ ፡ ከእጅ ፡ መንሻ ፡ ወገን ፡ አስቀ
ድሞ ፡ ስለሰጠ ፡ ባሏ ፡ ችግረኛ ፡ ቢሆን ፡ ከእርሱ

አንቀጽ ፡ ፳፱ ።

ዘት ፡ ዘከነ ፡ ላቲ ፡ እምውእቱ ፡ ኢይብሕዋ ፡
አላ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ትሴሰየሙ ፡ ለብእሲሃ ፡
ወለደቂቃ ፡ እምንዋየ ፡ ሕይሃ ።
፱፻፲፰ ገጽ ፡ ኀምስ ፡ ጠስ ፡ ፱ቱ ፡ ወለእመ ፡ እስተእኀዘ ፡
ብእሲ ፡ ንዋየ ፡ ብእሲቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ምክራ ፡
ኢይደሉ ፡ እጊዝ ፡ ወለእመኒ ፡ ሠምረት ፡ ብእ
ሲት ፡ ምንታ ፡ እንዘ ፡ ይትብር ፡ አኀዘ ፡ ንዋየ ፡
ወአርመመት ፡ ወእኀዘት ፡ ድኅረ ፡ ፈቲዳ ፡
ከመ ፡ ትትራዳእ ፡ በካልእ ፡ ኅቡረ ፡ እልባቲ ፡
ረድኤት ። እሰመ ፡ ሕግ ፡ ይረድእ ፡ ብእሲተ ፡
ሠናይተ ፡ ወእኮ ፡ እኪተ ።
፱፻፲፱ ገጽ ፡ ሳድስ ፡ በእንተ ፡ ከሊአ ፡ ኅድግተ ፡ ብእ
ሲት ፡ ዘእንበለ ፡ ዘተነግረ ፡ ባቲ ፡ በዘይመዐር ፡
አውሰበ ። ወውእቱ ፡ በከመ ፡ ሰምዐ ፡ ከነ ፡ በቲ ፡
ወንጌል ፡ ማቴዎስ ፡ በብሂሎቱ ። "ወመጽኡ ፡
ኀበ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ፈሪሳውያን ፡ ከመ ፡
ያመክርዎ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ይደልዎኑ ፡ ለብ
እሲ ፡ ከመ ፡ ይድኅር ፡ ብእሲቶ ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡
ምክንያት ፡ እውሥአ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ኢያን
በብክሙኑ ፡ ከመ ፡ ፈጠርሙ ፡ ቀዲሙ ፡ ተባዕተ ፡
ወአንስተ ። ወይቤ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ የኀድግ ፡
ብእሲ ፡ እባሁ ፡ ወእሞ ፡ ወይተልዋ ፡ ለብእ
ሲቱ ፡ ወይከውኑ ፡ ክልኤሆሙ ፡ ፩ደ ፡ ሥጋ ፡
ወዘእግዚአብሔር ፡ አስተፃመረ ፡ ኢይክል ፡
ይፍልጥ ፡ ሰብእ" ። ወይቤልዎ ፡ ለምንትኑ ፡
አዘዘ ፡ ሙሴ ፡ ከመ ፡ የሀብዋ ፡ መጽሐፈ ፡ ኅዳ
ጋቲሃ ፡ ወይድኅርዋ ። ወይቤሎሙ ፡ ሙሴሰ ፡
በእንተ ፡ እከየ ፡ ልብክሙ ፡ ጸሐፈ ፡ ለክሙ ፡
ከመ ፡ ትድኅኑ ፡ አንስቲያክሙ ፡ ወበፍጥረትሰ ፡
እኮ ፡ ከመዝ ። እንሰ ፡ እብለክሙ ፡ ከመ ፡
ኵሉ ፡ ዘይድኅር ፡ ብእሲቶ ፡ ዘእንበለ ፡ ትዝሙ ፡
ረሰያ ፡ ዘማ። ወእንተሂ ፡ ደኅራ ፡ ምታ ፡ ዘእው
ሰበ ፡ ዘመወ ። ወጳውሎስኒ ፡ ሐዋርያ ፡ ይቤ ፡
ዘቆሮንቶስ ፡ ፯ቱ ፡ ለይንበር ፡ ብእሲ ፡
ምስለ ፡ ብእሲቱ ፡ ወብእሲትኒ ፡ ትንበር ፡
ምስለ ፡ ምታ ። ወይቤ ፡ ካዕበ ፡ ወለእለሂ ፡ አው
ሰቡ ፡ አኮ ፡ አነ ፡ ዘእኤዝዘሙ ፡ ዳእሙ ፡ ትእ
ዛዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢትትፈለጥ ፡ ብእሲት ፡
ወእመሰ ፡ ፈቀደት ፡ ተፈልጦ ፡ ተዘሰ ፡ እንበለ ፡
ምት ፡ ወሰእመ ፡ እኮ ፡ ትትበረቅ ፡ ምስለ ፡
ምታ ፡ ወሰብእሲኒ ፡ ኢይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይኅ
ድግ ፡ ብእሲቶ ። ዘ፰ ፡ ወለእመሰ ፡ ኮንኩ ፡ አ ፡
ብእሲ ፡ እሡረ ፡ ምስለ ፡ ብእሲትከ ፡ ኢትፍ፡

ስለ ፡ ጋብቻ ።

የወሰደችውን ፡ ብትይዝ ፡ እይፍቀዱላት ። ከማ
ሜዋ ፡ ገንዘብ ፡ ልጆቿንና ፡ ባሏን ፡ ልትመግብ
ቸው ፡ ይገባል ፡ እንጂ ።
፱፻፲፰ ፭ኛው ፡ ክፍል ፡ ጠስ ፡ ፱ ። ባል ፡ የሚስቱን ፡
ገንዘብ ፡ ሳያማክራት ፡ መያዝ ፡ እድርጎ ፡ ቢያ
ሲዝ ፡ መያዝ ፡ እይገባም ። ሴት ፡ ባሏ ፡ ገንዘ
ቧን ፡ መያዝ ፡ ሲያደርግ ፡ ወድዳ ፡ ዝም ፡ ብት
ል ፡ ኋላ ፡ ከሌላ ፡ ጋራ ፡ በአንድነት ፡ ልትረዳ
በት ፡ ወዳ ፡ ብትይዝ ፡ ረዳት ፡ የላትም ። ሕግ ፡
ክፉዎቱን ፡ ያይደለ ፡ ደጎቱን ፡ ሴት ፡ ይረዳ
ልና ።
፱፻፲፱ ፮ኛው ፡ ክፍል ። ጋብቻ ፡ በሚሻርበት ፡ ገንዘብ ፡
ከተነገረበት ፡ በቀር ፡ ሚስት ፡ መፍታትን ፡
ስለመከልከል ፡ ይናገራል ። ይኸውም ፡ የማቴ
ዎስ ፡ ወንጌል ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ምስክር ፡ እንደ
ሆነበት ፡ ነው ። ፈሪሳውያን ፡ ስለምክንያቱ ፡
ሁሉ ፡ ሚስቱን ፡ ይፈታ ፡ ዘንድ ፡ ለሰው ፡ ይገ
ባዋልን ፡ እያሉ ፡ ይፈትኑት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ጌታ
ኢየሱስ ፡ መጡ ። ቀድሞ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡
አድርጎ ፡ እንደፈጠራቸው ፡ አላነበባችሁምን ?
ብሎ ፡ መለሰላቸው ። ስለዚህ ፡ ወንድ ፡ አባ
ቱንና ፡ እናቱን ፡ ትቶ ፡ ሚስቱን ፡ ይከተላታል ።
ሁለቱም ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ይሆናሉ ። እግዚአብ
ሔር ፡ አንድ ፡ ያደረጋቸውንም ፡ ሰው ፡ ሊለይ ፡
አይችልም ። ሙሴ ፡ የምትፈታበትን ፡ ደብ
ዳቤ ፡ ሰጥተው ፡ ይፈቷት ፡ ዘንድ ፡ ለምን ፡
አዘዘ ? አሉት ። ሙሴስ ፡ ስለልቡናችሁ ፡
ክፋት ፡ ሚስቶቻችሁን ፡ ትፈቱ ፡ ዘንድ ፡ ጻፈላ
ችሁ ። በተፈጥሮ ፡ ግን ፡ እንዲዚህ ፡ አይደለም ፡
አላቸው ። እኔ ፡ ግን ፡ ሳትሰስን ፡ ሚስቱን ፡
የሚፈታ ፡ ሁሉ ፡ እርሱ ፡ ዘማ ፡ አደረጋት ።
ባሏ ፡ የፈታትንም ፡ ያገባ ፡ አመነዘረ ። አላች
ኋለሁ ። (ማቴ ፡ ፲፱ ፡ ፫ - ፲) ። ሐዋርያ ፡ ጳው
ሎስም ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ቆሮ ፡ ፯ ። ባል ፡ ከሚ
ስቱ ፡ ጋራ ፡ ይኑር ። ሴትም ፡ ከባሏ ፡ ጋራ ፡
ትኑር ። ዳግመኛም ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ያገቡትን ፡
ሰዎች ፡ እኔ፡ የማዝዛቸው ፡ አይደለሁም ። የእግ
ዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ነው ፡ እንጂ ። ሴት ፡
አትፋታ ። ልትፋታ ፡ ብትወድ ፡ ግን ፡ ያለ
ባል ፡ ትኑር ። ያም ፡ ባይሆን ፡ ከባሏ ፡ ጋራ ፡
ትታረቅ ። ለወንድም ፡ ሚስቱን ፡ ሊፈታ ፡ አይ
ገባውም ። ፰ ። ሰው ፡ ሆይ ፡ ከሚስትህ ፡ ጋራ ፡
የታሠርክ ፡ ብትሆን ፡ ከእርሷ ፡ መለየትን ፡

አንቀጽ ፡ ፳፱ ።

ስለ ፡ ጋብቻ ።

ቅድ ፡ ተፈልጦታ ።

፻፳ ገጽ ፡ ሳብዕ ፡ በእንተ ፡ ከመ ፡ ኢይእበዩ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ለካልኡ ። ዘቆሮንቶስ ፡ ፯፡፫ ፡ ወለየሀብ ፡ ብእሲ ፡ ለብእሲቱ ፡ ፍቅረ ፡ ዘይደሉ ፡ ላቲ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወከማሁ ፡ ብእሲትኒ ፡ ካዕበ ፡ ትግበር ፡ ለምታ ። ወኢኮነት ፡ ብእሲት ፡ ብውሕተ ፡ ላዕለ ፡ ሥጋሃ ፡ አላ ፡ ምታ ፡ ብውሕ ፡ ላዕሌሃ ። ወከማሁ ፡ ብእሲኒ ፡ ኢኮነ ፡ ብውሐ ፡ ላዕለ ፡ ሥጋሁ ፡ አላ ፡ ለብእሲት ፡ ሥልጣን ፡ ላዕሌሁ ። ወኢይክልእ ፡ ፩ዱሂ ፡ እምኔክሙ ፡ ለቢጹ ፡ ፍቅረ ፡ ዘይደሉ ፡ ሎቱ ፡ ዳእሙ ፡ ሶበ ፡ ተሰናአውክሙ ፡ ለጾም ፡ ወለጸሎት ። ወእምዝ ፡ ግብኡ ፡ ሶበ ፡ ፈጸምክሙ ፡ ዘንተ ፡ ኀበ ፡ ፈቃድክሙ ፡ ከመ ፡ ኢይጽባእክሙ ፡ ሰይጣን ፡ በእንተ ፡ ኀጢአ ፡ ሥምረትክሙ ። እብለክሙ ፡ ዘንተ ፡ ከመ ፡ ዘይትበሃል ፡ ለድኩማን ፡ አኮ ፡ በትእዛዝ ፡ ምቱር ።

አትሻ ። (፩ኛ ፡ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፲፩ - ፳፰) ።

፻፳ ፯ኛው ፡ ክፍል ። ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ ሁለተኛውን ፡ እንቢ ፡ ሊለው ፡ ስለማይገባ ፡ ይናገራል ። ቆሮ ፡ ፯ ። ባል ፡ ለሚስቱ ፡ ከእርሱ ፡ ላይ ፡ ለእርሷ ፡ የሚገባውን ፡ ፍቅር ፡ ይስጥ ። ዳግመኛም ፡ ሚስት ፡ እንደዚሁ ፡ ለባሏ ፡ ታድርግ ። ሴት ፡ በገዛ ፡ ሥጋዋ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ የላትም ፡ ባሏ ፡ በራሷ ፡ ላይ ፡ የሠለጠነ ፡ ነው ፡ እንጂ ። ባልም ፡ እንደዚሁ ፡ በገዛ ፡ ሥጋው ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ የለውም ። በእርሱ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ለሚስቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ። ከእናንተ ፡ አንዱ ፡ ለጓደኛው ፡ ሊያደርግለት ፡ የሚገባውን ፡ ፍቅር ፡ አይከልክል ። ለጾም ፡ ለጸሎት ፡ በተስማማችሁ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ እንጂ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይህን ፡ በፈጸማችሁ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፈቃዳችሁ ፡ ተመለሱ ። የምትሹትን ፡ ስላጣችሁ ፡ ሰይጣን ፡ ድል ፡ እንዳይነሣችሁ ። ለደካሞች ፡ እንደሚነገር ፡ ይህን ፡ እላችኋለሁ ። በቍርጥ ፡ ትእዛዝ ፡ አይደለም ። (፩ኛ ፡ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፫ - ፯) ።

፻፳፩ ገጽ ፡ ሳምን ፡ በእንተ ፡ ዕለታት ፡ ዘኢይደሉ ፡ ይትራከቡ ፡ በሙ ፡ ብእሲ ፡ ወብእሲት ፡ ወተነግረ ፡ በቀኖናት ፡ እለ ፡ ይሰመያ ፡ ዘነገሥት ፡ ወከልኡ ፡ እምነ ፡ ተራክቦተ ፡ ወላድያኒሁ ፡ ለዘነሥእዎ ፡ በጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ እመኒ ፡ በመዓልት ፡ ወእመኒ ፡ በሌሊት ፡ በእንተ ፡ ክብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ።

፻፳፩ ስምንተኛው ፡ ክፍል ። ሴትና ፡ ወንድ ፡ ሊገናኙ ፡ ባቸው ፡ ስለማይገቡ ፡ ቀኖች ፡ ይናገራል ። ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ በሚባሉ ፡ መጻሕፍት ፡ ተነገረ ። በጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ ያነሡትን ፡ የልጁን ፡ ወላጆች ፡ ከመገናኘት ፡ ከለከሉ ። ስለ ፡ ክብረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ ቢሆን ።

፻፳፪ በስ ፡ ፲ወ፩ዱ ፡ ኢታርስሐን ፡ ለመዋዕላት ፡ ቅዱሳት ፡ እንተ ፡ ጾም ፡ ወበመዋዕለ ፡ ትክቶሃ ፡ ወሕርሳ ፡ ኢትቅረባ ፡ ከመ ፡ ኢይኩን ፡ ተዋስቦትከ ፡ ዘእንበለ ፡ ሕግ ። ተዘከር ፡ ዘአዘዘከ ፡ እግዚአብሔር ፡ በአፈ ፡ ሙሴ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ንግሮሙ ፡ ለደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ወበሎሙ ፡ ለእመ ፡ ቀርበ ፡ ፩ዱ ፡ ኀበ ፡ ብእሲት ፡ ትክት ፡ ይሠረዉ ፡ ወይሙቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ወልድ ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ኢያክበሩ ፡ አመ ፡ ወደዩ ፡ ዘርአ ፡ ንጹሐ ፡ ውስተ ፡ ደመ ፡ ትክቶሃ ። ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ግብር ፡ እዘዙ ፡ ይሙት ፡ ብእሲ ፡ ዘእንበለ ፡ ወልድ" ።

፻፳፪ በስ ፡ ፲፩ ። የተቀደሱ ፡ የጾም ፡ ወራቶችን ፡ አታሳድፋቸው ፡ በአራስነቷና ፡ በደምዋ ፡ ወራት ፡ አትገናኛት ። ጋብቻህ ፡ ያለ ፡ ሕግ ፡ እንዳይሆን ፡ እግዚአብሔር ፡ በሙሴ ፡ አንደበት ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ያዘዘህን ፡ አስብ ። አንድ ፡ ሰው ፡ ግዳጅ ፡ ወደ ፡ አገኛት ፡ ሴት ፡ ቢቀርብ ፡ ያለ ፡ ልጅ ፡ ይጥፉ ፡ ይሙቱም ፡ ብለህ ፡ ለእሥራኤል ፡ ልጆች ፡ ንገራቸው ። እነርሱ ፡ ንጹሑን ፡ ዘር ፡ ከግዳጅዋ ፡ ደም ፡ ውስጥ ፡ በመጨመራቸው ፡ አላከበሩምና ፡ (ዘሌ ፡ ፳ ፡ ፲፰) ። ስለዚህ ፡ ሥራም ፡ ወንድ ፡ ያለ ፡ ልጅ ፡ እንዲሞት ፡ አዘዙ ።

፻፳፫ ዘ፴ ፡ ወእሌ ፡ ሎቱ ፡ ለዘይገብራ ፡ ለዛቲ ፡ ኃጢአት ፡ በሰሙን ፡ ሕማማት ፡ ቅድስት ።

፻፳፫ ፴ ። በከበረች ፡ በሰሙነ ፡ ሕማማት ፡ ይችን ፡ ኃጢአት ፡ ለሚሠራት ፡ ወዮለት ።

፻፳፬ ዘ፴ወ፫ቱ ፡ ወስብሳብስ ፡ ዘወሀቦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለደቂቀ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ አኮ ፡ በእንተ ፡ ወሊደ ፡ ውሉድ ፡ ባሕቲቱ ፡ አላ ፡ በእንተ ፡

፻፳፬ ፴፫ ። እግዚአብሔር ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡ የሠራው ፡ ጋብቻ ፡ ግን ፡ ልጆችን ፡ ለመውለድ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። ስለማይጠበት ፡ ፈቃድም ፡

አንቀጽ ፡ ፳፱ ።

መፍቅድ ፡ ዘኢ.ዕቁብ ። መሠርዐ ፡ እግዚአብሔር ፩ደ ፡ ጊዜ ፡ ዘይትዐቀቦ ፡ ቦቱ ፡ ወ፩ደ ፡ ጊዜ ፡ ዘይገብሩ ፡ ቦቱ ፡ ፈቃዶሙ፡ ወባሕቱ ፡ ኢይኩን ፡ በርኵስ ።

፱፻፳፩ ክፍል ፡ ወተከልአስ ፡ አምነ ፡ ሩካቤ ፡ በመዋዕለ ትክቶሃ ፡ ወሕርሳ ፡ ዝኒ ፡ በእንተ ፡ ዘይረክቦ ፡ ለእባለ ፡ ዘርእ ፡ አሙስና ፡ ወዘይዳደቆሙ ፡ ለውሉድ ፡ እለ ፡ ተፀንሱ ፡ በከርሥ ፡ እምነ ፡ አንታክቲ ፡ ግብር ፡ ሕማመ ፡ ዝልጋሴ ።

፱፻፳፪ ሥርዋጽ ፡ ፳ወ፩ዱ ፡ ሀሎ ፡ በቀኖናት ፡ ዘንገሥት ፡ ዝልጋሴኒ ፡ ወለምጽኒ ። ወተከልአስ ፡ በመዋዕለ ፡ እጽዋም ፡ ዝኒ ፡ ከመ ፡ ይትፈጸም ፡ ከዊነ ፡ ፈቃድ ፡ ዘበእንተ ፡ ጾም ፡ ወውእቱኒ ፡ ከሊእ ፡ ነፍስ ፡ እንስሳዊት ፡ እምነ ፡ ፍትወት ፡ እንስሳዊት ፡ በእንተ ፡ ከብረ ፡ ነፍስ ፡ ነባቢት ፡ ዘትትወሐድ ፡ ባቲ ፡ በከመ ፡ ግእዘ ፡ ጠባይዓሃ ፡ መንፈሳዊት ፡ ወይደሉ ፡ ለኵሉ ፡ ለለ፩ዱ ፡ ከመ ፡ ይትከልእ ፡ በመዋዕለ ፡ ደም ፡ ዘየማስን፡ ለዐቂበ ፡ ሥጋሁ ፡ ወለዐቂበ ፡ ውሉዱ ። ወበስሙን ፡ ሕማማትኒ ፡ እስመ ፡ እማንቱ ፡ መዋዕለ፡ ኀዘን ፡ ወጾም ፡ ወጸሎት ፡ ብዙኅ ፡ ሌሊተ ፡ ወመዓልተ ። ወእለ ፡ ተርፋስ ፡ እጽዋም ፡ እመቦ ፡ ዘተመውዐ ፡ እምፍትወት ፡ ንዳዲት ፡ ወበኢይትከሀሎ ፡ ሳዕለ ፡ ተጋድሎታ ፡ ይደልዎ ፡ ለውቱ፡ ከመ ፡ ያትፍእ ፡ ኪያሃ ፡ ወያእትት ፡ ተጻድቆተ ፡ ሕሠማ ፡ በጊዜያተ ፡ ሌሊት ፡ ዘብውሕ ፡ ባቲ ፡ በሊዕ ፡ ወሰትዮ ፡ ዘእንበለ ፡ ሌሊተ ፡ መዓልት ፡ አንተ ፡ ባቲ ፡ ተእዘዘ ፡ ይቅረቦ ፡ ባቲ ።

፱፻፳፫ ገጽ ፡ ሣልስ ፡ በእንተ ፡ አሕርሞ ፡ ከዕወተ ፡ ዘርእ ፡ አፍእ ፡ እማሕፀነ ፡ ብእሲት ፡ ዘይከውን ፡ እመጽሐፍ ፡ ወልብ ። ቀዳሚሰ ፡ እስመ ፡ መፍቅድ ፡ ቀዳማዊ ፡ ዘኮነ ፡ በእንተ ፡ አውስቦ ፡ ኢኮነ ፡ ዘእንበለ ፡ በእንተ ፡ አትርፎ ፡ ዘርእ ፡ በከመ ፡ እቅድምነ ፡ ጥዩቀ ፡ ወትከውን ፡ አንከ ፡ ንሥኢ ፡ ብእሲት ፡ ምስለ ፡ እግኅሦተ ፡ ዘርእ ፡ ወዘይመስሎ ፡ ዘኢይትረከብ ፡ ባቲ ፡ ዘየኀሥሥ ፡ ኪያሁ ፡ ይደልዎ ፡ ለዘያወስብ ፡ ኅዲገ ፡ ንሢእ ፡ ብእሲት ።

፱፻፳፬ ወዳግምኒ ፡ መከ ፡ ፲ወ፫ቱ ፡ በእንተ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘይቤ ፡ በኦሪት ። እመቦ ፡ ብእሲ ፡

ስለ ፡ ጋብቻ ።

ነው ፡ እንጂ ። እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የሚጠበቁበትን ፡ አንድም ፡ ጊዜ ፡ ፈቃዳቸውን ፡ የሚፈጽሙበትን ፡ ሠራ ። ነገር ፡ ግን ፡ በርኵሰት ፡ አይሁን ።

፱፻፳፩ ክፍል ። ከሩካቤ ፡ መከልከል ፡ ግን ፡ በማዳጆዋና ፡ በአራስነቷ ፡ ወራት ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ዐባለ ፡ ዘርእን ፡ ከጥፋት ፡ ወገን ፡ ስለሚያገኘው ነው ። ከዚችም ፡ ሥራ ፡ የተነሣ ፡ በማኅፀን ፡ የተፀነሱትን ፡ ልጆች ፡ የሥጋ ፡ ደዌ ፡ ስለሚያገኛቸው ፡ ነው ።

፱፻፳፪ ሥርዋጽ ፡ ፳፩ ። በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ የሥጋ ፡ ደዌ ፡ ለምፅም ፡ አለ ። በጾም ፡ ወራት ፡ መከልከል ፡ ግን ፡ ስለጾም ፡ የሚሆነው ፡ የፈቃድ ፡ አኳኋን ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ እንስሳዊት ፡ ነፍስን ፡ ከፍትወት ፡ እንስሳዊት ፡ መከልከል ፡ ነው ። በእርሷ ፡ ተዋሕዳ ፡ ስላለች፡ ስለነባቢት ፡ ነፍስ ፡ ክብር ፡ እንደ ፡ መንፈሳዊት ፡ (ረቂቅ) ፡ ጠባይዋ ፡ ሥራ ። ሁሉም ፡ ለያንዳንዱ ፡ ሰውነቱንና ፡ ልጆቹን ፡ ለመጠበቅ ፡ አጥፊ ፡ በሆነ ፡ በደም ፡ ወራት ፡ ሊከለከሉ ፡ ይገባል ። በሰሙነ ፡ ሕማማትም ። እነዚህ ፡ በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ የኀዘን ፡ የጾም ፡ የብዙ ፡ ጸሎት ፡ ወራቶች ፡ ናቸውና ። በቀሩት ፡ አጽዋም ፡ ግን ፡ ከምታቃጥል ፡ ፍትወት ፡ የተነሣ ፡ ድል ፡ የሆነ ፡ ቢኖር ፡ ድል ፡ ሊነሣትም ፡ የማይቻለው ፡ ቢሆን ፡ ርሷን ፡ ሊያርቅ ፡ ይገባዋል ። መብል ፡ መጠጥ ፡ በተፈቀደባት ፡ በሌሊት ፡ ጊዜያቶች ፡ የፈቲው ፡ ጦርን ፡ ያርቅ ። ይቆርቡባት ፡ ዘንድ ፡ ከታዘዘባት ፡ የመዓልት ፡ ሌሊት ፡ በቀር ።

፱፻፳፫ ፫ኛ ፡ ክፍል ። ከሴት ፡ ማኅፀን ፡ አውጥቶ ፡ በአፍአ ፡ (በውጭ) ፡ ዘርዕ ፡ ማፍሰስን ፡ ስለመከልከል ፡ ይናገራል ። ይኸውም ፡ ከመጽሐፍና ፡ ከልብ ፡ የሚሆን ፡ ነው ። መጀመሪያው ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ጋብቻ ፡ የሆነው ፡ መጀመሪያው ፡ ፈቃድ ፡ አስቀድመን ፡ እንዳስረዳን ፡ ዘርን ፡ ለመተካት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አይጸናምና ። ዘርንና ፡ የሚመስለውን ፡ ከማራቅ ፡ ጋራ ፡ እንግዲህ ፡ ሚስት ፡ ማግባት ፡ እርሱን ፡ የሚፈልጉት ፡ የማይገኝበት ፡ ትሆናለች ። እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ ለሚያገባ ፡ ሰው ፡ ሚስት ፡ ማግባትን ፡ መተው ፡ ይገባዋል።

፱፻፳፬ ሁለተኛውም ፡ መከ ፡ ፲፫ ። በኦሪት ፡ ስለተነገረው ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይናገራል ።

ዘሰከበ ፡ ምስለ ፡ ብእሲት ፡ ወእግኅሠ ፡ ዘርአ ፡ እምኔሃ ፡ ኢይሕየው ፡ እምቀቲል ። ትእ ፡ ፳ወ ፲፥ ፡ ወእውናን ፡ ወልደ ፡ ይሁዳ ፡ ምስለ ፡ ብእ ሲት ፡ እኁሁ ፡ በከመ ፡ ይነግር ፡ መጽሐፍ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ኮነ ፡ ሶበ ፡ ተደመረ ፡ ያእትት ፡ ዘርአ ፡ እምኔሃ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ወጸንዐ ፡ ገቢረ ፡ ግብሩ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወቀ ተሎ ።

፱፻፳፱ ወይቤ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ በትርጓሜ ፡ ወንጌለ ፡ ማቴዎስ ፡ ወናሁ ፡ ይትጌበሩ ፡ ከመ ፡ ኢይኩን ፡ ለፍጥረቶሙ ፡ ፍሬ ። ወዝንቱ ፡ የአኪ ፡ እምተ ኃጥአቶሙ ፡ ለሀልዋን ፡ ወዝንቱ ፡ እከይ ፡ ከመ ፡ ይትኃጥኡ ፡ እለ ፡ ይሄልዉ ። ወዝንቱ ፡ ይከውን ፡ በእንተ ፡ እውፅአተ ፡ ዘርአ ፡ ወገዲ ፎቱ ፡ በኀበ ፡ ኢይከውን ፡ ዘርአ ፡ ወገቢረ ፡ ሥራይ ፡ በእንተ ፡ ክሊእ ፡ ፅንስ ።

፱፻፴ ገጽ ፡ ኀሥር ፡ ለነቦሱ ፡ ዘይፀርፍ ፡ በእንተ ፡ ሙስና ፡ መማ ፡ ፱ወ፳፥ ፡ ትሔ ፡ ዘ፲ወ፫ቱ ፡ ወሶበ ፡ እውሰበ ፡ ብእሲ ፡ እምኔከሙ ፡ ብእሲተ ፡ ወቦአ ፡ ኀቤሃ ፡ ወእምዝ ፡ ጸልአ ፡ በከንቱ ፡ ወይቤ ፡ ኢረከብኩ ፡ ድንግልናሃ ፡ ወለእመ ፡ ቆመ ፡ አቡሃ ፡ ወተፋትሐ ፡ በእንቲአሃ ፡ ወረ ከበ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ጸረፈ ፡ በሐሰት ፡ ይገሥ ጽዎ ፡ በእንተ ፡ ግብሩ ፡ ወይኩንንዎ ፡ በእንተ ፡ አበሳሁ ፡ ወትኩን ፡ ሎቱ ፡ ብእሲተ ፡ እመኒ ፡ ፈቀደ ፡ አው ፡ እበየ ። ወኢይትከሀሎ ፡ ከመ ፡ ይትፈለጥ ፡ እምኔሃ ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ይመውት ፡ ፩ዱ ፡ እምክልኤሆሙ ። ወእመሰ ፡ ኮነ ፡ ቃለ ፡ ፅርፈቱ ፡ እሙነ ፡ ወኢተረክበ ፡ ድንግልናሃ ፡ ወእልቦሙ ፡ አእምሮ ፡ ለወላድያኒሃ ፡ ወተዐ ውቀ ፡ ነገረ ፡ ኀፍረታ ፡ ይትፈለጡ ፡ ክልኤሆሙ ሙትከውን ፡ ርግምተ ፡ ወኢትትወሰብ ፡ ለካ ልእ ። ወትንበር ፡ በቢታ ፡ እንዘ ፡ ተኀዝን ፡ ወት በኪ ። እስመ ፡ ይእቲ ፡ ዘመወት ፡ በቤተ ፡ አቡሃ ፡ ወእስተኀፈረቶ ።

፱፻፴፩ መማ ፡ ፺ወ፯ቱ ፡ ትሔ ፡ ዘ፹ቱ ፡ ለእመቦ ፡ ብእሲ፡ ዘነገርዎ ፡ ሰብእ ፡ ከመ ፡ ዘመወት ፡ ብእሲቱ ፡ ወኢያእመረ ፡ ጥዩቀ ፡ ለዝንቱ ፡ ወፈቀደ ፡ ከመ ፡ ያእምር ፡ ጥዩቀ ፡ ግብራ ፡ ያብጽሓ ፡ ኀበ፡ ፈታሒ ፡ ዘቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለእግዚአብ ሔር ፡ ወያቅማ ፡ ቅድመ ፡ ምሥዋዕ ፡ ወይን ግእ ፡ ኪዳነ ፡ ሙዳየ ፡ ልሕኩት ፡ ወይደይ ፡ ውስቴቱ ፡ ማየ ፡ መሪረ ፡ ክብርታዊተ ፡ ወይ



ከሴት ፡ ጋራ ፡ የተኛ ፡ ዘሩንም ፡ ከእርሷ ፡ ያራቀ፡ ቢኖር ፡ ከሞት ፡ አይዳን ። ትእ ፡ ፳፯ ። የይሁዳ ፡ ልጅ ፡ አውናን ፡ ከወንድሙ ፡ ሚስት ፡ ጋር ፡ በተገናኘ ፡ ጊዜ ፡ ዘሩን ፡ ከእርሷ ፡ አውጥቶ ፡ በምድር ፡ ያፈሰው ፡ እንደነበረ ፡ ይህን ፡ ሥራ ውን ፡ መሥራቱም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በጸና ፡ ጊዜ ፡ እንደገደለው ፡ መጽሐፍ ፡ ይና ገራል ። (ዘፍ ፡ ፴፰ ፡ ፱ - ፲፩) ።

፱፻፳፱ አፈ ፡ ወርቅም ፡ በማቴዎስ ፡ ወንጌል ፡ ትርጓሜ እንዲህ ፡ አለ ። ለተፈጥሯቸው ፡ ልጅ ፡ እንዳይ ገኝ ፡ እነሆ ፡ ይጥራሉ ። ይህስ ፡ ከሉት ፡ መኃ ጣት ፡ ይከፋል ። ይህም ፡ ከፋት ፡ ያሉት ፡ ይኃ ጡ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ይህም ፡ ዘርን ፡ አውጥቶ ፡ በማይሆን ፡ ቦታ ፡ ሰለማፍሰስ ፡ ይሆናል ። ፅን ስንም ፡ ስለመከልከል ፡ ሥራይ ፡ በማድረግ ፡ ነው ።

፱፻፴ እሥረኛው ፡ ክፍል ፡ ስለጥፋት ፡ ለሚሳደብ ፡ ሁሉ ፡ ይናገራል ። መማ ፡ ፱ወ፳ ። ትሔ ፡ ፲፫ ። ከእ ናንተ ፡ ወገን ፡ ሰው ፡ ሚስት ፡ አግብቶ ፡ በደረሰ ባት ፡ ጊዜ ፡ ከዚሀ ፡ በኋላ ፡ በከንቱ ፡ ቢጠላት ፡ ድንግልናዋንም ፡ አላገኘሁም ፡ ቢል ፡ አባቷም ፡ ስለእርሷ ፡ ቆሞ ፡ ቢከራከርና ፡ እርሱ ፡ በሐሰት ፡ እንደሰደባት ፡ ቢያውቅ ፡ ስለሥራው ፡ ይገሥ ጹት ። ስለበደሉም ፡ ይቅጡት ። እሺ ፡ ቢል ፡ ወይም ፡ እንቢ ፡ ቢል ፡ ሚስት ፡ ትሁነው ። ከሁ ለቱ ፡ አንዱ ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ ከእርሷ ፡ ሊለይ ፡ አይቻለውም ። የስድቡ ፡ ቃል ፡ እው ነት ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ድንግልናዋም ፡ ባይገኝ ፡ ወላጆቿ ፡ ባያውቁ ፡ የሚያሳፍር ፡ ነገሯም ፡ ቢታ ወቅ ፡ ሁለቱ ፡ ይለያዩ ። የተረገመች ፡ ትሁን ። ስሌላም ፡ ሚስት ፡ አትሁን ። እያዘነችና ፡ እያለ ቀሰች ፡ በቤቷ ፡ ትኑር ፡ ባባቷ ፡ ቤት ፡ ስስና ፡ አሳፍራዋለችና ። (ዘዳ ፡ ፳፪ ፡ ፲፫ - ፳፩) ።

፱፻፴፩ መማ ፡ ፺፯ ። ትሔ ፡ ፰ ። ሚስቱ ፡ እንደሰሰነች ፡ ሰዎች ፡ የነገሩት ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ የዚህን ፡ እርግ ጡን ፡ ባያውቅ ፡ የሥራዋን ፡ እርግጠኛነት ፡ ሊያውቅ ፡ ቢወድ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዳኛ ፡ ያድርሳት ። ከምሥዋዑ ፡ ፊትም ፡ ያቁማት ። ኪዳኑ ፡ የሸክላ ፡ ገንቦ ፡ (መንቀል) ፡ ወስዶ ፡ የከበረች ፡ መራራ ፡ ውሀ ፡ በውስጧ ፡ ይጨምር ፡ ከምሥዋዑ ፡ ምድጃ ፡

ንግእ ፡ መሬተ ፡ እማእዘንተ ፡ ምሥዋዕ ፡ ወይ
ደዮ ፡ ውስተ ፡ ማይ ፡ ወየእኅዝ ፡ በእደዊሁ ፡
ወትክሥት ፡ ርእሳ ፡ ወያምሕላ ፡ በነይለ ፡
ታቦት ፡ ወበኀድረተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ላዕ
ሌሁ ፡ በከሉ ፡ ጊዜ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ዘመወኑ ፡
ምስሌኪ ፡ ብእሲ ፡ ነኪር ፡ ወሰእመ ፡ ትቤ ፡
አልቦ ፡ ይበሳ ፡ ካህን ፡ ሶበሰ ፡ ኮንኪ ፡ ንጽሕተ ፡
እምዝ ፡ ተሐዘበ ፡ ቦቱ ፡ ብእሲኪ ፡ ስትዩኪ ፡
ዘንተ ፡ ማየ ፡ ወአልቦ ፡ ዘይነክየኪ ፡ሕሡም ፡
ወእመሰኬ ፡ እንተ ፡ በበደኪ፡ ወመሐልኪ ፡ በሐ
ሰት ፡ ግዘተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትኀድር ፡ ላሰ
ሌኪ ፡ ወከኒ ፡ ዲወውተ ፡ እምሰብእ ፡ ቢትኪ ፡
ወዝንቱ ፡ ማይ ፡ ዘትሰትዩዮ ፡ ያማስን ፡ ኵሎ ፡
ሥጋኪ ፡ ወይምስ ፡ ኵሎ ፡ አባላተኪ ፡ ወኢይ
ጽናዕ ፡ ለዓለም ። ወትበል ፡ ብእሲት ፡ አሜን ፡
አሜን ፡ ወአሜን ፡ ወትሰቲዩ ፡ ውእቱ ፡ ማየ ፡
በቅድመ ፡ ምሥዋዐ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዘ ፡
ክሡት ፡ ርእሳ ፡ ወምታ ፡ እንዘ ፡ ይሬእያ ፡ በእሰ
ይንቲሁ ። ወሰእመ ፡ ኮነት ፡ ሐሳዊተ ፡ ውእቱ ፡
ማይ ፡ ዘሰትየቶ ፡ ይነፍኅ ፡ ኵሎ ፡ ሥጋሃ ፡ ወት
ከውን ፡ ትእምርተ ፡ ለኵሉ ፡ ዘይሬእያ ፡ ወእ
መሰ ፡ ኮነት ፡ ንጽሕተ ፡ እይረክባ ፡ ምንትኒ ፡
ሕሡም ፡ ወይእቲ ፡ ትፀንስ ፡ ወትወልድ ፡
ወልደ ፡ ብእሴ ፡ ዘትትፌሣሕ ፡ ቦቱ ፡ ወያእ
ትት ፡ እግዚአብሔር ፡ እምታ ፡ ዘወድቀ ፡
ውስተ ፡ ልቡ ፡ እምትሕዝብት ፡ ወትንእት ፡
ዘላሰሊሃ ።

፱፻፴፪ ገጽ ፡ ዓሥር ፡ ወ፩ዱ ፡ በእንተ ፡ እእምሮተ ፡
ግብር ፡ እንተ ፡ ትከውን ፡ ለእእምሮተ ፡ አው
ስቦ ፡ ወእምኔሃ ፡ ኢይደልዎ ፡ ለ፩ዱሂ ፡ ከመ ፡
የሐሊ ፡ ከመ ፡ አውሰቦ ፡ ሕሩም ፡ ውእቱ ፡ ወኢ
ግብራቲሁ ። ረስጠጅ ፡ ፵ወ፰ቱ ፡ ወዘሰ ፡ ተከ
ልአ ፡ እምእውሰቦ ፡ እመንገለ ፡ እስተራኵሶ ፡
ሁብድ ፡ ውእቱ ፡ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ዘፈጠሮ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ሠናይ ፡ ውእቱ ፡ ጥቀ ። እስመ ፡
ተባዕተ ፡ ወአንስተ ፡ ዘፈጠረ ፡ እግዚአብሔር ፡
ሰሠናይ ፡ ወሰአዳም ፡ ወለይትመተር ፡ እም
ቤተ ፡ ክርስቲያን ። ወለእመሰ ፡ ኮነት ፡ ተከ
ልአቱ ፡ በእንተ ፡ ፍና ፡ ተፀምዶ ፡ ወንጽሕ ፡
ሰዝንቱሰ ፡ ብጹሕ ፡ ሎቱ ።

፱፻፴፫ ማንር ፡ ፩ዱ ፡ ወዘእንወረ ፡ ሥርዓተ ፡ እውሰቦ ፡
ዘበእማን ፡ ወይቤ ፡ ከመ ፡ ቀረቦቱ ፡ ርኩስ ፡
ወከመ ፡ ይእቲ ፡ ትከልእ ፡ በዊእ ፡ መንግሥተ ፡



ሐመድ ፡ ወስዶ ፡ ከውዘው ፡ ይጨምረው ።
በእጁም ፡ ይያዘው ። ራሷን ፡ ትግለጽ ። በታ
ቦቱ ፡ ኃይልና ፡ ሁልጊዜ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ በአ
ደረው ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ያምላት ። እንዲህ፡
እያለ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ካንቺ ፡ ጋራ ፡ አመነዘረን ? ።
የለም ፡ ብትል ፡ ባልሽ ፡ ከተጠራጠረበት ፡ ነገር
የነጻሽ ፡ ከሆንሽ ፡ ይህን ፡ ውሀ ፡ ጠጪ ። የሚጎ
ዳሽ ፡ ክፉ ፡ ነገርም ፡ የለም ፡ ይበላት ። እንቺ ፡
ስንፈሽ ፡ በሐሰት ፡ ብትምዪ ፡ ግን ፡ የእግዚአብ
ሔር ፡ እርግማን ፡ በላይሽ ፡ ላይ ፡ ትደር ። ከቤ
ተሰቦችሽም ፡ የተለየሽ ፡ ሁኚ ። ይህ ፡ የምትጠ
ጪው ፡ ውሀ ፡ ሰውነትሽን ፡ ያጥፋው ። ሰውነ
ትሽን ፡ ሁሱ ፡ ያቅልጠው ። ለዘለዓለም ፡ አይ
ጽና ። ሴቲም ፡ አሜን ፡ አሜን ፡ አሜን ፡ ትበል
በምሥዋዑ ፡ ፊት ፡ ስፊት ፡ ቆማ ፡ ራሷን ፡
ገልጣ ፡ ባሏ ፡ በዓይኑ ፡ እያየት ፡ ያንን ፡ ውሀ ፡
ትጠጣ ፡ ሐሰተኛ ፡ ብትሆን ፡ የጠጣችው ፡ ውሀ
ሰውነቷን ፡ ሁሉ ፡ ይነፋዋል ። ላያትም ፡ ሁሉ ፡
ምልክት ፡ (መቀጣጫ) ፡ ትሆናለች ። የነፃች ፡
ብትሆን ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አያገኛ
ትም ። እርሷ ፡ ትፀንሳለች ። ደስ ፡ የምትሰኝበ
ትም ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ትወልዳለች ። በእርሷ ፡
ላይ ፡ ካደረገው ፡ በትንዓትና ፡ ከጥርጥር ፡ ወገን፡
በልቡ ፡ ውስጥ ፡ የወደቀውን ፡ እግዚአብሔር ፡
ከባሏ ፡ ያርቃል ። (ዘኊ ፡ ፭ ፡ ፲፩ - ጽ፫) ።

፱፻፴፪ አሥረኛ ፡ ክፍል ። ጋብቻን ፡ ለማወቅ ፡ የም
ትሆን ፡ ሥራን ፡ ስለማወቅ ፡ ይናገራል ። ከእር
ሷ ፡ የተነሣ ፡ ለአንዱስ ፡ እንኳ ፡ ጋብቻ ፡ ሥራ
ዎቹም ፡ የተከለከለ ፡ እንደሆነ ፡ ሊያስብ ፡ አይገባ
ውም ። ረስጠጅ ፡ ፵፰ ። በማራከስ ፡ ከጋብቻ ፡
የተከለከለ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ አላዋቂ ፡ ነው ። እግዚ
አብሔር ፡ የፈጠረው ፡ ሁሉ ፡ እጅግ ፡ መልካም፡
ነውና ። እግዚአብሔር ፡ ሴትና ፡ ወንድ ፡ አደ
ርጎ ፡ የፈጠረ ፡ ለመልካም ፡ ነገር ፡ ነውና ፡
ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይለይ ። መከልከሉ ፡ ስለ ፡
ንጽሕናና ፡ ስለምንኵስና ፡ ብትሆን ፡ ግን ፡ ለእ
ርሱስ ፡ ይገባዋል ።

፱፻፴፫ ማንር ፡ ፩ ። እውነተኛውን ፡ የጋብቻ ፡ ሥርዓት ፡
የነቀፈ ፡ ወደእርሷም ፡ መቅረብ ፡ ርኵስ ፡ ነው ፡
እርሷም ፡ ወደመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ መግባትን

ሰማያት ፡ ውጉዝ ፡ ውእቱ ።

፱፻፵፬ ዘ፲ወ፬ቱ ፡ ወዘሂ ፡ ኀደገ ፡ ብእሲቶ ፡ ወይፈቱ ፡ ከመ ፡ ትትዋሰቦ ፡ እምኔሁ ፡ እንዘ ፡ ይረክቦ ፡ ለአውስቦ ፡ ውጉዝ ፡ ውእቱ ። ወዓዲ ፡ ኢብ ሔሕ ፡ ከመ ፡ ትባእ ፡ ትክት ፡ እው ፡ ሐራስ ፡ መወልዲት ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በጊ ዜያት ፡ እንተ ፡ ናመጽእ ፡ ዘክሮቶን ።

፱፻፵፭ ዘኒቅያ ፡ ዘ፳ወ፱ቱ ፡ ኢትባእ ፡ ትክት ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወኢትቅረብ ፡ እስከ ፡ ይት ፌጸም ፡ መዋዕለ ፡ ትክቶሃ ፡ ወእመኒ ፡ ኮነት ፡ ብእሲተ ፡ ንጉሥ ፡ ወእመሂ ፡ ካህን ፡ ዘተዐይወ ፡ ዘንተ ፡ ለይደይ ፡ እመዓርጊሁ ።

፱፻፵፮ በዲድ ፡ ፲ወ፰ቱ ፡ ወብእሲትኒ ፡ እንተ ፡ ወለ ደት ፡ ትንበር ፡ በአፍአ ፡ እመካን ፡ ቅዱስ ፡ ፵ ፡ ዕለተ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ተባዕተ ፡ ወእመሰ ፡ ወለ ደት ፡ አንስተ ፡ ፹ ፡ ዕለተ ። ወመወልዳትኒ ፡ ኢይትመጠዋ ፡ እምሥጢራት ፡ እስከ ፡ ይክ ውን ፡ ፳ ፡ ዕለት ፡ በተባዕት ፡ ወ፵ ፡ ዕለት ፡ በአ ንስት ።

፱፻፵፯ ወካዕበ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይትገኃሡ ፡ እምዘማ ዊት ። በስ ፡ ፲ወ፫ቱ ፡ ወብእሲት ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ምት ፡ ሶበ ፡ ዘመወት ፡ ወኢየእመረ ፡ ባቲ ፡ ብእሲሃ ፡ ይደልዋ ፡ ነሥኦ ፡ ለባሕቲታ ፡ እመሰ ፡ አእመረ ፡ ባቲ ፡ ምታ ፡ ወኢፈቀደ ፡ ይስድዳ ፡ ይሰደዱ ፡ ክልኤሆሙ ።

፱፻፵፰ ዘ፲ወ፩ቱ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ካዐኒ ፡ ይትመተር ፡ እምሢመቱ ፡ ወይክልእዎ ፡ እምሥጢራት ። ወሶበ ፡ ነስሐ ፡ እምድኅረ ፡ ተመትረ ፡ እምሢ መቱ ፡ ወሰደዳ ፡ ለይእቲ ፡ ይመይጥዎ ፡ እምሥ ጢራት ፡ ወባሕቲቱ ፡ ኢይትመየጥ ፡ ኀበ ፡ ሢመቱ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ተሳተፈ ፡ ዘማዊተ ።

፱፻፵፱ ዘ፵ወ፩ዱ ፡ ወለእመ ፡ ተወሰበት ፡ ብእሲተ ፡ ቀሲስ ፡ ለካልእ ፡ እምድኅረ ፡ ሞቱ ፡ እስመ ፡ ንብረት ፡ ፳ዕለተ ፡ ወወሀበት ፡ ሕጸጸ ፡ ለመ ዓርግ ፡ ቀዳሚት ፡ ይደልዋ ፡ ንስሐ ።

፱፻፶ ምዕራፍ ፡ ፯ ። በእንተ ፡ ዘይመዐር ፡ ተዋስቦ ፡ ተዋስቦሰ ፡ ይመዐር ፡ በ፫ቱ ፡ ግብራት ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ እመ ፡ መንክሩ ፡ በሥምረቶሙ ፡ ብእሲ ፡ ወብእሲት ፡ ኅቡረ ።

፱፻፶፩ ወዳግምኒ ፡ ይእዜኒ ፡ ተመይጠ ፡ ኀበ ፡ ኀርየተ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ወውእቱ ፡ ከመ ፡ ይዕበዩ ፡



ትክለክላለች ፡ የሚል ፡ የተለየ ፡ ነው ።

፱፻፵፬ ፲፬ ። ሚስቱን ፡ የፈታ ፡ ጋብቻን ፡ እያረከሰ ፡ ከእርሱ ፡ እንድትለይ ፡ የሚወድም ፡ የተለየ ፡ ነው ። ዳግመኛም ፡ ከግዳጅ ፡ ያልነጻች ፡ ወይም ፡ አራስ ፡ ወይም ፡ ያዋለደች ፡ ሴት ፡ ስማ ቸውን ፡ ወደፊት ፡ በምናመጣው ፡ ጊዜያቶች ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንድትገባ ፡ አይፈቀድም ።

፱፻፵፭ ኒቅያ ፡ ፳፱ ። ደም ፡ የሆነች ፡ ሴት ፡ ወደ ፡ ቤተ ክርስቲያን ፡ አትግባ ። የግዳጅዋም ፡ ወራት ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ አትቅረብ ። የንጉሥ ፡ ሚስትም ፡ (እቴጌም) ፡ ብትሆን ፡ ይህን ፡ የተ ዳፈረ ፡ ካህን ፡ ቢኖር ፡ ከሹመቱ ፡ ይሻር ።

፱፻፵፮ በዲድ ፡ ፲፰ ። የወለደች ፡ ሴትም ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ቢሆን ፡ ፵ ፡ ቀን ፡ ሴት ፡ ብትወልድ ፡ ግን ፡ ፹ ፡ ቀን ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በአፍአ ፡ ትቆይ ። አዋላጆችም ፡ በወንድ ፡ ልጅ ፡ እስከ ፡ ኻያ ፡ ቀን ፡ በሴት ፡ እስከ ፡ ፵ ፡ ቀን ድረስ ፡ ከሥ ጋውና ፡ ከደሙ ፡ አይቀበሉ ።

፱፻፵፯ ዳግመኛ ፡ ከአመንዝራ ፡ ሴት ፡ ይርቁ ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ። በስ ፡ ፲፫ ። ባል ፡ ያላት ፡ ሴት ፡ ብት ስስን ፡ ባሏም ፡ ቢያውቅባት ፡ ለብቻዋ ፡ ንስሐ፡ ይገባታል ። ባሏ ፡ ቢያውቅባት ፡ ግን ፡ ሊፈታ ትም ፡ ባይወድ ሁለቱም ፡ ይለዩ ።

፱፻፵፰ ፲፩ ። ካህን ፡ ቢሆን ፡ ከሹመቱ ፡ ይሻር ። ከምሥ ጢራትም ፡ ይከልክሉት ። ከሹመቱ ፡ ከተሻረ ፡ በኋላ ፡ ቢጸጸት ፡ እርሷንም ቢፈታት ፡ ሥጋው ንና ፡ ደሙን ፡ ያቀብሉት ። ነገር ፡ ግን ፡ ወደሹ መቱ ፡ አይመለስ ። ከዘማዊቱ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ሁኗልና ።

፱፻፵፱ ሣ፩ ። የቄስ ፡ ሚስት ፡ ከባሏ ፡ ሞት ፡ በኋላ ፡ ለሌላ ፡ ሚስት ፡ ብትሆን ፡ ለደገኛይቱ ፡ መዓ ርግ ፡ ስድብን ፡ (ተዋርዶን) ፡ ጉድለትንም ፡ ስለ ሰጠች ፡ ንስሐ ፡ ይገባታል ።

፱፻፶ ስድስተኛ ፡ ምዕራፍ ። ጋብቻ ፡ ስለሚፈርስበት፡ ይናገራል ። ጋብቻ ፡ በሦስት ፡ ነገሮች ፡ ይፈር ሳል ። ከእነርሱም ፡ አንዱ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ተስማምተው ፡ በአንድነት ፡ ቢመነኩሱ ፡ ነው ።

፱፻፶፩ ሁለተኛውም ፡ ከእነርሱ ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ምርጫ መመለስ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ጋብቻን ፡ ከሚከለ

ለቢጹ ፡ እምተደምሮ ፡ ከመ ፡ ይደመሩ ፡ ተደምሮተ ፡ መፍቅድ ፡ ለተዋስቦ ፡ በገጸት ፡ ዝኩራት፡ በክፍል ፡ ሳምን ፡ እምዘ ፡ ይከልእ ፡ እውሰቦ ። እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ኢይከውን ፡ ምስሌሁ ፡ መፍቅድ ፡ ቀዳማዊ ፡ በእውስቦ ፡ ወውእቱ ፡ ረኪበ ፡ ዘርእ ፡ ይእበዮ ፡ ለቢጹ ፡ እምተደምሮቱ ፡ ወእኩ ለመፍቅድ ፡ ዘተላዊሁ ፡ ሎቱ ፡ ወውእቱ ፡ እሰስሎተ ፡ ሕማመ ፡ ፍትወት ፡ ላዕለ ፡ ገጽ ፡ ዘኢትከልአ ፡ ሕግ ። ወይተልዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ተመትሮተ ፡ ዜና ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዓመታተ ፡ ብዙኀ ፡ በምክንያተ ፡ ተሞቅሖቱ ፡ ወዘይመስሎ ።

፱፻፵፪ ወኀልሰኒ ፡ ዘኢይትፈጸም ፡ ቦቱ ፡ ፈቃድ ፡ ካልእ ፡ በእውስቦ ፡ ወውእቱ ፡ ተራድኦቶሙ ፡ በእንተ ፡ እቅልሎተ ፡ ሕይወት ፡ ወእሠንዮታ ። ወዝንቱኒ ፡ ይትከፈል ፡ ኀበ ፡ ፪ቱ ፡ እክፍል እው ፡ ለ፩ዱ ፡ ዘይደሉ ፡ እምውስቴን ፡ ዘእውስቦ ፡ ዘቀዳሚሃ ፡ ወዘይኄሪሃ ፡ ስቦ ፡ ጽንዐ ፡ ድቀተ ፡ ዝሙቱ ፡ ኀበ ፡ ብእሲት ፡ ወበዝን ፡ ድቀቱ ፡ በካልእት ፡ እምብእሲቱ ፡ ይትኄነይሃ ።

፱፻፵፫ ወዳግምኒ ፡ ኢይደሉ ፡ ዝሙት ፡ ፈድፋደ ፡ በከመ ፡ ተጠየቀ ። ለዝንቱ ፡ ክልኤ ፡ ክፍላት ፡ በእንተ ፡ ዘይከውን ፡ ቦሙ ፡ ሙስና ፡ ሕይወቶሙ ፡ ዘኀጢአ ፡ ሲሲት ፡ እምቀቢጸ ፡ እስተሐምሞተ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ለካልኡ ፡ ወኢበውሉዶሙ ፡ እምዘ ፡ ይከውን ፡ መፍቅዳቲሆሙ ፡ ወእስተሐምሞቶሙ ፡ ስዘዘልፈ ፡ ይትቄረኖሙ ፡ ኩሎ ፡ ጊዜ ፡ በኑኀ ፡ ሕይወቶሙ ፡ ወይትመየጥ ፡ ጸግዎ ፡ ንዋዩ ፡ ኀበ ፡ ነኪራን ። ውኀጢአ ፡ ጠይቆተ ፡ ብእሲ ፡ ለዘርእ ፡ ዚእሁ ፡ ወይከውኖ ፡ ወራሲ ፡ ካልእ ፡ ወልድ ፡ ዘኢተወልደ ፡ እምኔሁ ። ወከመ ፡ ኢይረስ ፡ ለዝንቱ ፡ ዘተወልደ ፡ እምዝሙት ፡ ስወሳዲሁ ፡ ዘበእማን ፡ ወይከውን ፡ ብጽሐተ ፡ ቀትል ፡ ላዕለ ፡ ፩ዱ ፡ እምውስቴን ፡ እው ፡ በዘማዊ ፡ ካልበ ፡ እመኒ ፡ በምክንያተ ፡ ቅንአት ፡ እው ፡ ለ፩ዱ ፡ ዘይደሉ ፡ ከመ ፡ ያስተዋስቦ ፡ ለ፩ዱ ፡ እምዘማውያን ፡ ካልእን ፡ በእስተዋስቦ ፡ እው ፡ በካልአቲሃ ።

፱፻፵፬ ወኀልስ ፡ እሕስሞቱ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ላዕለ ፡ ሕይወቱ ፡ ካልኡ ፡ ወበተጋሰዮተ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ምስለ ፡ ካልኡ ፡ ይከውን ፡ ጋእዝ ፡



ክል ፡ ወገን ፡ በስምንተኛው ፡ ክፍል ፡ በተነገሩት ፡ ሥራዎች ፡ ለጋብቻ ፡ የሚያሻውን ፡ መገናኘት ፡ ይገናኙ ፡ ዘንድ ፡ ከመገናኘት ፡ ኋይኛውን ፡ ይከለክለው ፡ ዘንድ ፡ ነው ። በጋብቻ ፡ መጀመሪያው ፡ ፈቃድ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ እያሆን ምና ። ይኸውም ፡ ዘርን ፡ ማግኘት ፡ ነው ። ከመገናኘት ፡ ባልንጀራውን ፡ እንቢ ፡ ቢለው ። እርሱን ፡ ለሚከተለው ፡ ፈቃድ ፡ እያደለም ። ይኸውም ፡ ሕግ ፡ በማትከለክለው ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ የፈተው ፡ ጡርን ፡ ማራቅ ፡ ነው ። ብዙ ፡ ዓመት ፡ በመታሠሩ ፡ በሚመስለውም ፡ ምክንያት ፡ ከእነርሱ ፡ ወገን ፡ ያንዱ ፡ ወሬ ፡ መቋረጥ፡ ይህን ፡ ይመስላል ።

፱፻፵፪ ሦስተኛውም ፡ በጋብቻ ፡ ጊዜ ፡ ሌላ ፡ ፈቃድ ፡ የማይፈጸምበት ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ኑሮን ፡ ለማቃለልና ፡ ለማሳመር ፡ መረዳዳታቸው ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ከ፪ ፡ ወገን ፡ ይከፈላል ። ወይም ፡ ከተጋቡት ፡ ላንዱ ፡ የሚገባ ፡ መጀመሪያይቱን ፡ ኹለተኛይቱን ፡ ያገባ ፡ ሰው ፡ በሚስቱ ፡ የዝሙቱ ፡ አወዳደቅ ፡ ቢጸና ፡ ከሚስቱም ፡ በሌላ ይቱ ፡ ሴት ፡ አወዳደቅ ፡ ቢበዛ ፡ ይፈርሳል ።

፱፻፵፫ ሁለተኛውም ፡ እንደተነገረ ፡ ዝሙት ፡ ፈጽሞ ፡ አይገባም ። ለዚህ ፡ ሁለት ፡ ክፍሎች ፡ አሉት ። ፍላጎታቸውና ፡ አሳባቸው ፡ በሕይወታቸው ፡ ዘመን ፡ ሁልጊዜ ፡ አዘውትሮ ፡ ለሚቃወማቸው ፡ በመሆኑ ፡ ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ ለሌላው ፡ ወይም ፡ በልጆቻቸው ፡ ማሰብን ፡ ከማጣት ፡ የተነሣ ፡ ምግብን ፡ በማጣት ፡ የሕይወታቸው ፡ ጥፋት ፡ ስለሚሆንባቸው ፡ ነው ። የገንዘቡ ፡ ስሁታም ፡ ወደሌሎች ፡ ይመለሳል ። ሰው ፡ ዘሩን፡ መረዳት ፡ ስለሚያጣና ፡ ከእርሱ ፡ ያልተወለደ ፡ ሌላ ፡ ልጅ ፡ የሚወርሰው ፡ ስለሆነ ፡ ነው ። በዝሙት ፡ የተወለደው ፡ እውነተኛ ፡ አባቱን ፡ እንዳይወርሰው ፡ ነው ። ከባልና ፡ ከሚስት ፡ ባንዱ፡ ወይም ፡ ዳግመኛ ፡ በዘማዊው ፡ ላይ ፡ ሞት ፡ የሚደርስ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ። በቅንዓት ፡ ምክንያትም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ከሌሎች ፡ አመንዝራዎች ፡ ለአንዱ ፡ አንዱን ፡ ያጋባው ፡ ዘንድ ፡ በሚያበቃ ፡ በጋብቻም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ በሌሎቹ ።

፱፻፵፬ ሦስተኛውም ፡ ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ በሌላው ፡ ሕይወት ፡ ላይ ፡ ክፋ ፡ ቢያደርግ ፡ ነው ። ከእነርሱም ፡ አንዱ ፡ ከሁለተኛው ፡ ጋራ ፡ በመከራ

ዘይሰተርአይ ፡ ቦቱ ፡ ግብረ ፡ ዓመፃ ፡ እኩይ ፡ ዘውስቴቱ ፡ ለልወት ።

፩፻፸፭ ወነዋ ፡ ተሠርዑ ፡ በእንተ ፡ እሉ ፡ ምግባራት ፡ ፫ቱ ፡ ቀኖናት ፡ ወዛቲ ፡ ይእቲ ። ቀዳማዊ ፡ ጠስ ፡ ዘ፲ወ፩ዱ ፡ እውሰበ ፡ ይፀራዕ ፡ ለእመ ፡ መንኰሰ ፡ ብእሲ ፡ ወብእሲት ፡ ኅቡረ ፡ በሥምረ ቶሙ ፡ ወዳግማዊኒ ፡ እውስቦ ፡ ይሠዐር ፡ በምክንያተ ፡ ዕጸብ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ብእሲ ፡ ዘኢ ይትከሀሎ ፡ ከመ ፡ ይደመር ፡ ምስለ ፡ ብእሲቱ ፡ ወይግበር ፡ ዘይደሉ ፡ ለፍጥረቱ ፡ እላ ፡ ይንበር ፡ እምድኅረ ፡ ተራክቦ ፡ እስከ ፡ ፫ቱ ፡ ዓመት ። ወእመ ፡ ፈጺመ ፡ ኢተከሀሎ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ዘረቀደ ፡ ይደሉ ፡ እሚሃ ፡ ለብእሲት ፡ ወለወላ ድያኒሃ ፡ ከመ ፡ ይሥዐሩ ፡ ተደምሮቶሙ ፡ ለእመ ፡ ኮነት ፡ ብእሲት ፡ ዘኢትፈትድ ፡ ነዲረ፡ ምስሌሁ ፡ ተሀበ ፡ ለብእሲ ፡ ሕፃሃ ፡ ለእመ ፡ ይነሥእ ፡ እምብእሲቱ ። ወእም፡ንሰ ፡ በቀደመ ፡ እምነ ፡ መርዓ ፡ ይትርፍ ፡ ኀበ ፡ ብእሲ ፡ ወኢ የሀብ ፡ ምንተኒ ፡ እምኔቢሁ ።

፩፻፸፮ መጅ ፡ ፩ቱ ፡ ወእመ ፡ ኮነ ፡ ብእሲ ፡ ዘእውሰበ ፡ ብእሲተ ፡ ወረከባ ፡ ሕጽጽተ ፡ እምፍጥረተ ፡ አንስት ፡ ወፍሉጥ ፡ ግብራ ፡ እምፍጥረታ ፡ ዘኢትማኅፆ ፡ ለብእሲ ፡ ወነገረ ፡ ዘንተ ፡ ውእቱ በቀዳሚት ፡ ዕለት ፡ በዊእቱ ፡ ኀቤሃ ፡ አው ፡ በሳኒታሁ ፡ አው ፡ በሣልስ ፡ ወነገሮ ፡ ለካህን ፡ ግብራቲሃ ፡ ንጽሕት ፡ ርእሱ ፡ እምለዳ ። ወሶበ ፡ ተግህደ ፡ ጥያቄሁ ፡ ይደልዎ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ከመ ፡ ይፍልጦሙ ፡ ወይፍታሕ ፡ ሥርዓታቲ ሆሙ ፡ ወያብሖ ፡ ለብእሲ ፡ እውስቦ ፡ ወትትገሠሥ ፡ ብእሲት ፡ ወይክልእዋ ፡ እምእውሰቦ ፡ ወይትሎሥሥዎ ፡ ለመላኪሃ ፡ ወየውግዝዎ ፡ እም ቍርባን ፡ ወእምበዊአ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ብዙኀ ፡ መዋዕለ ።

፩፻፸፯ ሀለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘአእመረ ፡ ውንብአ ፡ ግብረ ፡ ዚአሃ ፡ ወተንበለ፡ ላዕለ ፡ ገቢረ ፡ ግብረ ፡ ኀፍረት ፡ መዋለለ ፡ ነዋኑ ፡ ወተከሥተ ፡ ግብራ ፡ እምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ይትገሠጽ ፡ ውእቱ ። ወእመ ፡ ኮነ ፡ ውእቱ ፡ እምዝ ፡ ይትዐቀብ ፡ ርእሶ ፡ ወይትዓገሥ ፡ በፍኖተ ፡ ንጽሕና ፡ ኢያብሕዎ ፡ እውስቦ ። ወለእመሰ ፡ ኮነ ፡ እምዝ ፡ ይትፈራህ ፡ ላዕሌሁ ፡ እምሐዊር ፡ ኀበ ፡ ዘየአኪ ፡ ኀፍረት ፡ እምዝ ፡ ሀለወ ፡ ቦቱ ፡ ለያብሕዎ ፡ እውስቦ ።



ክር ፡ በውስጡ ፡ ሽፍጥ ፡ ያለበት ፡ ክፉ ፡ የዓመፅ ፡ ሥራ ፡ የሚገለጽበት ፡ ክርክር ፡ ይሆናል ።

፩፻፸፭ ስለእነዚህ ፡ ሥራዎች ፡ እነሆ ፡ ፫ ፡ መጻሕፍት ፡ ተጽፈዋል ። መጀመሪያይቱም ፡ ይህች ፡ ናት ። ጠስ ፡ ፲፩ ። ባልና ፡ ሚስት ፡ በፈቃዳቸው ፡ አንድነት ፡ ቢመነኰሱ ፡ ጋብቻ ፡ ይፈርሳል ። ሁለተኛውም ፡ ጋብቻ ፡ በጭንቅ ፡ ምክንየት ፡ ይፈርሳል ። ወንድ ፡ ለተፈጥሮው ፡ የሚገባውን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ከሚስቱ ፡ ጋራ ፡ መገናኘት ፡ የማይቻለው ፡ ቢሆን ፡ ከመገናኘት ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ ፫ ፡ ዓመት ፡ ይኑር ፡ እንጂ ። የወደደውን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ፈጽሞ ፡ ባይቻለው ፡ ያንጊዜ ፡ ለሚስቲቱ ፡ ለወላጆቿም ፡ ጋብቻውን ፡ ሊያፈርሱ ፡ ይገባል ። ሴቲቱ ፡ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ ማደርን ፡ የማትወድ ፡ ብትሆን ፡ ከሚስቱ ፡ የሚቀበል ፡ ከሆን ፡ ማጫዋን ፡ ትስጠው ፡ ከሠርግ ፡ የቀደመው ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ግን ፡ ከሰውየው ፡ ዘንድ ፡ (ከእማቱ) ይቅር ። ከዚያው ፡ ውስጥም ፡ አይስጥ ።

፩፻፸፮ መጅ ፡ ፩ ። ሚስት ፡ ያገባ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ከሴቶችም ፡ ተፈጥሮ ፡ ጕድላ ፡ ቢያገኛት ፡ ከፍጥረቷ ፡ የተነሣ ፡ ለወንድ ፡ የማትመች ፡ ሥራዋ ፡ ልዩ ፡ ቢሆን ፡ ወደርሷ ፡ በመግባቱ ፡ በመጀመሪያዋ ፡ ቀን ፡ እርሱ ፡ ይህን ፡ ቢናገር ፡ በማግስቱ ፡ ወይም ፡ በሣልስቱ ፡ ሁኔታዋን ፡ ለካህኑ ፡ ቢነግረው ፡ ራሱ ፡ ከዕዳ ፡ ነፃ ። እርግጡ ፡ በታወቀ ፡ ጊዜ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሊለያቸው ፡ ውላቸውን ፡ ሊያፈርስላቸው ፡ ይገባዋል ። ለወንዱ ፡ እንዲያገባ ፡ ይፍቀድለት ። ሴቲቱ ፡ ግን ፡ ትቀጣ ። ከማግባትም ፡ ይከልክሏት ። አሳዳጊዋንም ፡ ይቅጡት፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከመግባት ቍርባንንም ፡ ከመቀበል ፡ ይከልክሉት ።

፩፻፸፯ እጡቆ ፡ ነውሯን ፡ ስውሮ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ የሚያሳፍር ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፡ ላይ ፡ የተደፋፈረ ፡ ቢሆን ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጥፋቷ ፡ ቢታወቅ ፡ እርሱም ፡ ይቀጣ ። ራሱ ፡ የሚጠበቅ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ በንጽሕና ፡ መንገድ ፡ የሚታገሥ ፡ ቢሆን ፡ እግባ ፡ አይበሉት ። ካለበት ፡ ሁኔታ ፡ ወደ ፡ ሚፈራ ፡ ኀፍረት ፡ ከመሄድ ፡ የተነሣ ፡ ከሚፈራው ፡ ወገን ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ቢሆን ፡ እግባ ፡ ይበሉት ።

አንቀጽ ፡ ፳፬ ።

፱፻፵፰ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘይነሥእ ፡ ጋእን ፡ ወለዝንቱኒ ፡ ፪ቱ ፡ ቃላት ። ቀዳሚ ፡ መ፲፪ ዘ፳ቱ ፡ ወእመ ፡ ረከባ ፡ ለብእሲቱ ፡ እንዘ ፡ ይነ ጽሕ ፡ ጋእን ፡ ወእመ ፡ ኮነ ፡ ዝንቱ ፡ ግብር ፡ ሐዲሰ ፡ ድኅረ ፡ በዊእታ ፡ ኀቤሁ ፡ ወነቢሮታ ፡ ምስሌሁ ፡ መዋዕለ ፡ ነዋኀ ፡ ደለወ ፡ ላዕሌሁ ፡ ፀዊሮታ ፡ ወተዓግሦታ ። እስመ ፡ ለውእ ቱኒ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ቦቱ ፡ ከመዝ ፡ እምይ ለወ ፡ ላዕሌሃ ፡ ፀዊሮቱ ፡ ወተዓግሦ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወእምኢያብሕዋ ፡ ላቲ ፡ ትትወሰብ ፡ ለካልእ ። ወለእመሰ ፡ ኮነ ፡ ላቲ ፡ ዝንቱ ፡ ግብር ፡ ወይ እቲ ፡ እንዘ ፡ ፍኅርት ፡ እምቅድመ ፡ በዊእታ ፡ ኀቤሁ ፡ ወተነበአ ፡ ግብራ ፡ እምኔሁ ፡ ወኢያእ መረ ወፈቀደ ፡ ኀዲጎታ ፡ ለይሠዐር ፡ ሎቱ ፡ ለአ ውስቦቱ ፡ ካልእታ ፡ ወይደሉ ፡ ላቲ ፡ ሕዳጌ ፡ ወትሎታ ፡ ወኵሉ ፡ ዘአምጽአት ፡ ሎቱ ፡ እም ቤተ ፡ አቡሃ ። ወለእመኒ ፡ አምጽአት ፡ ምስ ሌሃ ፡ እምእንስሳ ፡ ትንግእ ፡ ኪያሆሙ ። ለዘኒ ማኅፀ ፡ እምኔሆሙ ፡ ትንግእ ፡ ዓዲ ፡ እምኀቤሁ ፡ እመ ፡ ሀለወ ፡ ወበዘሞቱሰ ፡ አልቦቱ ፡ ዕዳ ፡ በላ ዕሌሁ ። ወእለሰ ፡ ተወልዱ ፡ እምነ ፡ እንስሳ ፡ ወኵሉ ፡ ዘረብኑ ፡ እምኔሆሙ ፡ ወእምፀምራ ፡ ወኵሉ ፡ ዘተወልዱ ፡ ውሉደ ፡ አግብርት ፡ ወአ እማት ፡ መንፈቁ ፡ ይኩን ፡ ላቲ ፡ ወካልእ ፡ መን ፈቁ ፡ ይኩን ፡ ለምታ ፡ ወዝኒ ፡ ለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ውእቱ ፡ ኀዲጎታ ። ወእመቦ ፡ ብእሲ ፡ ዘኮነ ማእከሌሁ ፡ ወማእከለ ፡ ብእሲቱ ፡ ፍልጠት በግብር ፡ እምእሉ ፡ ግብራት ፡ ወሶበ ፡ በልዐ ምንተኒ ፡ እምትሎታ ፡ ትንግእ ፡ ዘዮንቱሁ ማኅፀ ፡ በከመ ፡ አምሳሊሁ ። ወለእመሰ ፡ ኮነ ዘጸሐፈ ፡ ላቲ ፡ ምንተኒ ፡ እምንዋዩ ፡ ኢይደልዎ የሀብ ፡ ላቲ ፡ አላ ፡ ይኩን ፡ ሎቱ ።

፱፻፵፱ ወዳግማዊ ፡ መግ ፡ ፸፱ቱ ፡ ወእመሰ ፡ ኮነ ፡ ሕማም ፡ ዘያወድቅ ፡ እኁዞ ፡ እምድኅረ ፡ ምጽ እታ ፡ ኀቤሁ ፡ ወእምከመ ፡ ፈቀደ ፡ ኀዲጎታ ፡ ትንግእ ፡ ሕዳጌ ፡ ወትሎታ ። ወለእመ ፡ ረከባ ዝኩ ፡ እምቅድመ ፡ ያውስባ ፡ ወኢያእመረ ፡ ዘንቱ ፡ ምታ ፡ እመ ፡ ፈቀደ ፡ ተፈልጦታ ፡ የሀባ ፡ ኵሎ ፡ ትሎታ ። ወዘሰ ፡ ጸሐፈ ፡ ላቲ ቦቱ ፡ እምነ ፡ ንዋዩ ፡ ዚአሁ ፡ ውእቱ ።

፱፻፶ ወለእመ ፡ እኁዞ ፡ ዝልጋሴ ፡ ለ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ፀ ፡ ፪ኤ ፡ ፍናዊት ። ቀዳማዊ ፡ መ፳ ፡ ፳ቱ ፡ ወለ እመ ፡ እኁዞ ፡ ዝልጋሴ ፡ ለ፩ዱ ፡ እምክልኤ

ስለ ፡ ጋብቻ ።

፱፻፵፰ ከእነርሱ ፡ አንዱን ፡ ጋኔን ፡ የሚይዘው ፡ ቢሆን ፡ ለዚህ ፡ ሁለት ፡ ነገሮች ፡ አሉት ። መጀ ፡ ፳ ። ሚስቱን ፡ ጋኔን ፡ ሲይዛት ፡ ቢያገኛት ፡ ይህ ፡ ሥራ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ከመግባቷ ፡ ብዙ ፡ ቀንም ፡ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ ከመኖሯ ፡ በኋላ ፡ አዲስ ፡ ነገር ቢሆን ፡ ሊረዳትና ፡ ሊታገሣት ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ተገባ ። ለእርሱም ፡ እንደዚህ ፡ ቢሆንበት ፡ በእ ርሷም ፡ ላይ ፡ ልትረዳውና ፡ ልትታገሠው ፡ በተገባ ፡ ነበርና ። ለሌላም ፡ ሚስት ፡ እንድት ሆን ፡ ባልፈቀዱላትም ፡ ነበርና ። ታጭታ ፡ ሳለ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ ከመግባቷ ፡ በፊት ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ያገኛት ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ሥራዋ ፡ ከእርሱ ፡ ተሰውሮ ፡ ያላወቀም ፡ ቢሆን ፡ ሊፈታትም ፡ ቢወድ ፡ ሊያይቱን ፡ ለማግባት ፡ ውሉ ፡ ይፍ ረስለት ። ማጫዋና ፡ ትልወቷ ፡ ከአባቷ ቤት ፡ ያመጣችለት ፡ ሁሉ ፡ ለእርሷ ፡ ይገባል ። ከከብት ፡ ወገን ፡ ከእርሷ ፡ ጋር ፡ ብታመጣም ፡ እነርሱን ፡ ትውሰድ ። ከእነርሱም ፡ ወገን ፡ የሸ ጠው ፡ ካለ ፡ ዳግመኛ ፡ ከዋጋው ፡ ትውሰድ ። በሞተው ፡ ግን ፡ ዕዳ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ የለበትም። ከእንስሳም ፡ ወገን ፡ የተወለዱት ፡ ከእነርሱም ፡ የረቡት ፡ ሁሉ ፡ ከጠጕራቸውም ፡ ከወንዶችና ፡ ከሴቶች ፡ ባሮች ፡ የተወለዱት ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ እኩሌታው ፡ ለእርሷ ፡ ሁለተኛው ፡ እኩሌታ ፡ ለባሏ ፡ ይሁን ። ይኸውም ፡ እርሱ ፡ ሊፈታት ፡ ቢወድ ፡ ነው ። ከእነዚህ ፡ ሥራዎች ፡ የተነሣ ፡ በሚስቱና ፡ በእርሱ ፡ መካከል ፡ በግድ ፡ መለ ያየት ፡ የሆነበት ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ከትልወቷ ፡ ምንም ፡ ቢበላ ፡ ስለእርሱ ፡ ፈንታ ፡ እንደመ ሰሉ ፡ ዋጋውን ፡ ትውሰድ ። ከገንዘቡ ፡ ምንም ፡ የጻፈላት ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ለእርሷ ፡ ሊሰጣት ፡ አይገባውም ። ለእርሱ ፡ ይሁንለት ፡ እንጂ ።

፱፻፵፱ ሁለተኛው ፡ መግ ፡ ፸፱ ። የሚጥላት ፡ ሕማም ፡ ወደእርሱ ፡ ከመምጣቷ ፡ በኋላ ፡ የያዛት ፡ ቢሆን ግን ፡ ሊፈታት ፡ ቢወድ ፡ ማጫዋንና ፡ ትልወ ቷን ፡ ትውሰድ ። ይህ ፡ ሳያገባት ፡ አስቀድሞ ፡ ቢያገኛት ፡ ባሏ ፡ ይህን ፡ ባያውቅ ፡ ሊፈታት ፡ ቢወድ ፡ ትልወቷን ፡ ሁሉ ፡ ይስጣት ። ከገንዘቡ ወገን ፡ ግን ፡ የጻፈላት ፡ ቢኖር ፡ የርሱ ፡ ነው ።

፱፻፶ ከእነርሱ ፡ አንዱን ፡ ደዌ ፡ ሥጋ ፡ ቢይዘው ፡ ሁለት ፡ አስተያየት ፡ አለው ። መጀመሪያው ፡ መጀ ፡ ፳ ። ከተጋቡ ፡ በኋላ ፡ ከሁለቱ ፡ አንዱን፡

ሆሙ ፡ እምድኅረ ፡ ተዋሰቡ ፡ ቶሙ ፡ ወፈቀደ
፩ዱ ፡ ከመ ፡ ይትፈለጥ ፡ እምካልኡ ፡ ኢኮነ
ዝንቱ ፡ ብውሒ ፡ ሎቱ ።

፱፻፶፩ ወዳግማዊ ፡ መክ ፡ ፳ወ፫ቱ ፡ ወውእቱ ፡ ዘይ
ደሉ ፡ ወዘእውስበ ፡ ብእሲተ ፡ ወእምዝ ፡ ኮነ ፡
ባቲ ፡ ድኅረ ፡ ተዋስቦታ ፡ ውስተ ፡ ሥጋሃ
ደዌ ፡ ዘከመ ፡ ዝልጋሴ ፡ ወለምጽ ፡ ወእመ
ውእቱ ፡ ፈቀደ ፡ ተፈልጦታ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡
የሀባ ፡ ኩሎ ፡ ትሎታ ፡ ወሕጻሃ ። ወለእመ ፡
ኢፈቀደ ፡ ተፈልጦታ ፡ ብውሕ ፡ ሎቱ ፡ እን
ብሮታ ፡ በተሰናእዎ ፡ ከመ ፡ የሀባ ፡ ላቲ ፡
ሲሳያ ፡ በእምጣነ ፡ ክሂሎቱ ፡ እምንዋዩ ፡
እስመ ፡ ዘኮነ ፡ ላዕሌሃ ፡ ኢኮነ ፡ በፈቃዳ ፡ ወኢ
በፈቃዱ ፡

፱፻፶፪ ጠስ ፡ ፲ወ፩ዱ ፡ ወንኤዝዝ ፡ እብጥሎተ ፡ ተዋ
ስቦ ፡ ለዘሀሎ ፡ ውስተ ፡ እሥረት ፡ ወባሕቱ ፡
እስከ ፡ ይትዐወቅ ፡ ብእሲ ፡ ወብእሲት ፡ የሀልዉ
ወንሕነ ፡ ንኅድግ ፡ ተደምሮ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜሃ ፡
ወኢይኩን ፡ ተዋስቦ ፡ ዳግማዊ ፡ ኢ ፡ ለእንስት ፡
ወኢ ፡ ለእደው ። ወእመ ፡ ተነበሉ ፡ ይገሥጽ
ዎሙ ፡ ለብእሲኒ ፡ ይንሥኡ ፡ እምኔሁ ፡ እምታ ፡
ዘእምቅድመ ፡ መርዓ ፡ ወለብእሲትኒ ፡ ይንሥኡ ፡
እምኔሃ ፡ ሕጻሃ ፡ ወትሎታ ። ወእመሰ ፡ ኮነ ፡ በኀ
ቡእ ፡ ለእመ ፡ ቦኑ ፡ ሀለወ ፡ ብእሲ ፡ በሕይወቱ
ዘእንትዝ ፡ በእደ ፡ ጸላኢሁ ፡ እው ፡ እልቦ ፡
ይእተ ፡ ጊዜ ፡ ይደልዎ ፡ ለብእሲ ፡ አው ፡ ለብእ
ሲት ፡ ከመ ፡ ይትዓገሡ ፡ ፭ተ ፡ ዓመተ ። ወእ
ምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ለእመ ፡ ተጠየቀ ፡ ግብረ
ሞቱ ፡ አው ፡ ርኅቀቱ ፡ ወተኀብአ ፡ ይደሉ ፡
እንከ ፡ እስተዋስቦ ፡ ዘእንበለ ፡ ፍርሃት ፡ ይት
ዐወቅ ፡ ድልው ፡ አውስቦ ፡ ለእመ ፡ አስተርአየ
እምድኅረ ፡ ውእቱ ፡ ግብረ ፡ ተወፍዮት ፡ አው ፡
ተሰወረ ።

፱፻፶፫ ዘ፲ወ፰ቱ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ብእሲሁ ፡ እምሐራ ፡
ንጉሥ ፡ ንሕነ ፡ ንኤዝዝ ፡ ከመ ፡ ይጽንሑ ፡
መጠነ ፡ ፬ቱ ፡ ዓመታት ፡ ዘይከውን ፡ ባቲ ፡
ዘሚት ፡ ወይትዓገሥ ፡ እንስቲያሆሙ ፡ ወለ
እመ ፡ ኢመጽአ ፡ ኀቤሆን ፡ እምኀቤሆሙ
ክታብ ፡ ወኢበጽሐ ፡ ኀቤሆን ፡ ዜና ። ወለእመ
ሰምዐት ፡ እሐቲ ፡ እምኔሆን ፡ ከመ ፡ ምቱ
ሞተ ፡ ኢይደልወን ፡ ናብሕ ፡ ላቲ ፡ ከመ ፡ ታው
ስብ ፡ ዘእንበለ ፡ ትጠይቅ ፡ ለሊሃ ፡ አው ፡ ወላይ ፡
ያኒሃ ፡ አው ፡ ካልእኒሆሙ ፡ ኀበ ፡ መኳንንት ፡



ደዌ ፡ ሥጋ ፡ ቢያዘው ፡ እንዱ ፡ ከሁለተኛው ፡
ሊለይ ፡ ቢወድ ፡ ይዘ ፡ ለእርሱ ፡ የተፈቀደ ፡
አይደለም ።

፱፻፶፩ ሁለተኛውም ፡ መክ ፡ ፳፫ ። ይህም ፡ የሚገባ ፡
ነው ። ሚስት ፡ ያገባ ፡ ሰው ፡ ከመጋባቷ ፡ በኋላ
በሥጋዋ ፡ ውስጥ ፡ ደዌ ፡ ቢያድርባት ፡ ይኸውም ፡
እንደ ፡ ደዌ ፡ ሥጋ ፡ እንደ ፡ ለምጽ ፡ ያለ ፡
ነው ። እርሱ ፡ ሊፈታት ፡ ቢወድ ፡ ትልወቷን
ንና ፡ ማጫዋን ፡ ሁሉ ፡ ሊሰጣት ፡ ይገባዋል ።
ሊለያት ፡ ባይወድም ፡ በተቻለው ፡ መጠን ፡
ምግቢን ፡ ከገንዘቡ ፡ እንዲሰጣት ፡ በመስማማት
ሊያኖራት ፡ ይገባዋል ። በእርሷ ፡ ላይ ፡ የሆ
ነው ፡ በፈቃዷ ፡ ወይም ፡ በፈቃዱ ፡ አልሆነ
ምና ።

፱፻፶፪ ጠስ ፡ ፲፩ ። በእሥራት ፡ ሳለ ፡ ሰው ፡ የጋብቻን ፡
መፍረስ ፡ እናዝዛለን ። ነገር ፡ ግን ፡ እስኪታወቅ
ድረስ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ይኑሩ ። (ይጠብቁ) ፡
እስከ ፡ መጨረሻዋ ፡ ድረስ ፡ መገናኘትን ፡ እኛ ፡
እንከለክላለን ። ለሴቶችም ፡ ለወንዶችም ፡ ሁለ
ተኛ ፡ ጋብቻ ፡ አይገባም ። ቢያፋፈሩ ፡ ግን ፡
ይቅጧቸው ። ከወንዱ ፡ ከሠርግ ፡ አስቀድሞ ፡
የመጣውን ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ይውሰዱ ። ከሴ
ቷም ፡ ማጫዋንና ፡ ትልወቷን ፡ ይውሰዱ ።
በስውር ፡ ቢሆን ፡ በጠላቱ ፡ እጅ ፡ የተያዘው
ሰው ፡ በሕይወቱ ፡ ቢኖር ፡ ወይም ፡ ያንጊዜ
ባይኖር ፡ ለወንድ ፡ ወይም ፡ ለሴት ፡ አምስት
ዓመት ፡ ሊታገሡ ፡ ይገባቸዋል ። ከዚህ ፡
በኋላ ፡ የሞቱ ፡ ነገር ፡ (ዜና) ፡ ወይም ፡ ርቆ
መሄዱ ፡ ቢታወቅም ፡ ባይታወቅም ፡ እንግዲህ
ያለ ፡ ፍርሃት ፡ ማጋባት ፡ ይገባል ። ከዚህ
ከመቀበል ፡ ሥራ ፡ በኋላ ፡ ቢገለጽም ፡ ቢሠወ
ርም ፡ ማግባት ፡ እንዲገባ ፡ ይታወቃል ።

፱፻፶፫ ፲፰ ። ሰውየው ፡ ከንጉሥ ፡ ጭፍራ ፡ ወገን ፡
ቢሆን ፡ ዘመቻ ፡ የሚሆንባት ፡ ሁለት ፡ ዘመት ፡
ያህል ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ እኛ ፡ እናዝዛለን ።
ሚስቶቻቸውም ፡ ይታገሡ ። ከባሎቻቸው
ዘንድ ፡ ወደእነርሱ ፡ ደብዳቤ ፡ ባይመጣ ፡
ወሬም ፡ ባይደርሳቸው ፡ ከእነርሱ ፡ እንዲቱ ፡
ባላ ፡ እንደሞተ ፡ ብትሰማ ፡ እርሷ ፡ ሳትረዳ ፡
ወይም ፡ ወላጆቿ ፡ ወይም ፡ ለሌሎች ፡ ባላ ፡
ማገልገልን ፡ ከሚያገለግላቸው ፡ ከመኳንንቱ ፡
ዘንድ ፡ ስለ ፡ ወሬው ፡ እርግጠኛ ፡ ሳትጠይቅ ፡

አንቀጽ ፡ ፳፱ ።

መልእክተ ፡ አንተ ፡ ኮነ ፡ ይትለአኮሙ ፡ ምታ ፡ ወትስእሎሙ ፡ በእንተ ፡ ጥያቄ ፡ ዜናሁ ። ወእመ ፡ ሞተ ፡ ይኩን ፡ ወንጌል ፡ ቅዱስ ፡ በቅድሜሆሙ ፡ ኀቡረ ፡ ለስምዕ ፡ ወእምድኅረ ፡ ጸንዐ ፡ ጥያቄሁ ፡ ትንሣእ ፡ ብእሲት ፡ መጽሐፈ ፡ መባሕት ፡ በዘይትዐወቅ ፡ ቦቱ ፡ ስማዕታት ፡ ላቲ ፡ ወእምድኅረዝ ፡ ትትዐገሥ ፡ ፩ደ ፡ ዓመተ ፡ ወእምዝ ፡ ይደልዋ ፡ ከመ ፡ ትትወሰብ ፡ ተዋስቦ ፡ ሕጋዊ ። ወእመሰ ፡ ተንበለት ፡ ወተወስደ ፡ ወት ፡ ዘንተ ፡ ይእቲኒ ፡ ወዘያወስባ ፡ ይትገሠጹ ፡ ከመ ፡ ተማኅጸ ፡ ዘማውያን ። ወሰማዕታት ፡ ጥያቄ ፡ ለእመ ፡ ኮኑ ፡ ስምዐ ፡ በሐሰት ፡ ይደቁ ፡ እመዓርጊሆሙ ፡ ወየሀቡ ፡ ፲ተ ፡ ልጥረ ፡ ወርቅ ፡ ወይኩን ፡ ለዘሐሰዉ ፡ በእንተ ፡ ሞቱ ። ወእምዝ ፡ ይደልዎ ፡ ለውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ዘነረየ ፡ እመ ፡ ይፈቅድ ፡ ትትመየጥ ፡ ኀቤሁ ፡ ይንሣእ ፡ ብእሲቶ ።

፬፻፶፬ ወሣልስኒ ፡ ይትከፈል ፡ ኀበ ፡ ፫ቱ ፡ ክፍላት ፡ ቀዳሚ ፡ በእንተ ፡ ዝሙታ ፡ ለብእሲት ። ጠስ ፡ ዘ፲ወ፩ዱ ፡ ወለእመ ፡ አእመረ ፡ ብእሲ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ይትከሀሎ ፡ ከመ ፡ ያቅም ፡ ስምዐ ፡ ጥያቄ ፡ ምስለ ፡ ብእሲቱ ፡ ከመ ፡ ይእቲ ፡ ዘመወት ፡ ይደልዎ ፡ ቅድመ ፡ ከመ ፡ ያቅም ፡ ዘንተ ፡ እሚሃ ፡ ይደልዎ ፡ ኀዲጎታ ። ወይንሣእ ፡ ብእሲ ሕዜሃ ፡ መጠነ ፡ ካዕበት ፡ ምስለ ፡ እምኃ ፡ ዘቀደመ ፡ ሎመርዓ ። ወለእመ ፡ አልቦቱ ፡ ውሉድ ፡ ይንሣእ ፡ እምንዋየ ፡ ብእሲት ፡ መጠነ ፡ ፫ቱ ፡ እድ ፡ እምትሎታ ። ወለእመሰ ፡ ቦቱ ፡ ውሉድ ፡ እምኔሃ ፡ ለይኩን ፡ ትሎታ ፡ ወዘተርፈ ፡ ንዋያ ፡ ዕቁበ ፡ ለውሉዳ ። ወእምድኅረዝ ፡ ሶበ ፡ ተከሥተ ፡ ግብረ ፡ ዝሙት ፡ በላዕሌሃ ፡ ይትኮነኑ ፡ ውእቱ ፡ ወይእቲ ፡ ኅቡረ ። ወለዘማዊኒ ፡ ዘዘመወ ፡ በብእሲቱ ፡ ይንሥእ ፡ እምኔሁ ፡ መጠነ ትሎት ፡ ዘወሀባ ፡ ቀዳሚ ፡ በጊዜ ፡ መርዓ ። ወለእመ ፡ ቦቱ ፡ ካዕበ ፡ ብእሲት ፡ ለዘማዊ ፡ ለትንሣእ ፡ ሕፄሃ ፡ ምስለ ፡ እምኃ ፡ ዘእምቅድመ ፡ መርዓ ፡ ወእመኒ ፡ ዘየ ፡ ሀለዉ ፡ ውሉድ ፡ ኢይኩን ፡ ለብእሲ ፡ ዘእንበለ ፡ ተግባረ ፡ ዚአሁ ፡ ወንዋይሰ ፡ የሀሉ ፡ በተዐቅቦ ፡ ለውሉዶሙ ። ወዘሀሎ ፡ ለብእሲ ፡ እምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ እምነ ፡ ጥሪት ፡ ንሕነ ፡ ንሁቦሙ ፡ ለውሉድ ፡ ወእምኃስ ፡ ዘእምቅድመ ፡ መርዓ ፡ ንኤዝዝ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ለብእሲት ፡ ለእመ ፡ ኢሀለዉ ፡ ውሉድ ፡ ወተረፈ ፡ ጥሪቱ ፡ ይኩን ፡ በማእከል ።

ስለ ፡ ጋብቻ ።

እንድታገባ ፡ ልናስናብታት ፡ አይገባንም ። ቢሞትም ፡ ቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ ለምስክርነት ፡ በፊታቸው ፡ ይኑር ። እርግጠኛነቱ ፡ ከታወቀ ፡ በኋላ ፡ ሴትዮዋ ፡ ለእርሷ ፡ የመሰከሩላት ፡ ምስክሮች ፡ በሚታወቁበት ፡ ገንዘብ ፡ የስንብት ፡ ደብዳቤ ፡ ትቀበል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ትታገሥ ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ ልታገባ ፡ ይገባታል ። ይህን ፡ ብትደፍ ፈርና ፡ ብትተላለፍ ፡ ግን ፡ እርሷም ፡ የሚያገባ ትም ፡ እንደ ፡ ዘማውያን ፡ ቅጣት ፡ ይቀጡ ። ያስረዱትም ፡ ምስክሮች ፡ በሐሰት ፡ የመሰከሩ ፡ ቢሆኑ ፡ ከመዓርጋቸው ፡ ይዋረዱ ። ፲ ፡ ወቄት ፡ ወርቅ ፡ ይስጡ ። በሞቱ ፡ ምክንያት ፡ ለዋሹ በት ፡ ሰው ፡ ይሁን ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ለዚያ ፡ ሰው ፡ የመረጠውን ፡ ሊያደርግ ፡ ይገባዋል ። ወደእርሱ ፡ ልትመለስ ፡ ቢወድ ፡ ሚስቱን ፡ ይውሰድ ።

፬፻፶፬ ፫ኛውም ፡ ከሦስት ፡ ክፍል ፡ ይከፈላል ። መጀመሪያው ፡ ስለሴት ፡ ዝሙት ፡ ይናገራል ። ጠስ ፡ ፲፩ ። እርሷ ፡ እንደስሰነች ፡ ከሚስቱ ፡ ጋራ ፡ የማስረጃ ፡ ምስክር ፡ ያቆም ፡ ዘንድ ፡ እንደሚቻለው ፡ ቢያውቅ ፡ አስቀድሞ ፡ ይህን ፡ ሊወስን ፡ ይገባዋል ። ያንጊዜ ፡ ሊፈታት ፡ ይገባዋል ። ባል ፡ ማጫዋን ፡ ለሠርግ ፡ ከቀደመው ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ጋራ ፡ በእጠፊታ ፡ ይውሰድ ። ልጅ ፡ ባይኖረው ፡ ከሴት ፡ ገንዘብ ፡ ወገን ፡ ከትል ወቷ ፡ ፫ ፡ እጅ ፡ ያህል ፡ ይውሰድ ። ከእርሷ ፡ ልጆች ፡ ቢኖሩት ፡ ግን ፡ ትልወቷና ፡ የቀረ ፡ ገንዘቧ ፡ ለልጆቿ ፡ የተጠበቀ ፡ ይሁን ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በእርሷ ፡ ላይ ፡ የዝሙት ፡ ሥራ ፡ በገለጠ ፡ እርሱም ፡ እርሷም ፡ በአንድነት ፡ ይቀጡ ። በፊታት ፡ ሚስቱ ፡ ሲሰስን ፡ የተገኘ ፡ አመንዝ ራም ፡ በሠርግ ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ ፡ በስጣት ፡ ትልሠት ፡ ልክ ፡ ከእርሱ ፡ ይውሰዱ ። ዳግመ ኛም ፡ ለአመንዝራው ፡ ሰው ፡ ሚስት ፡ ብትኖ ረው ፡ ከሠርግ ፡ በፊት ፡ ከተሰጠው ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ጋራ ፡ ማጫዋን ፡ ትውሰድ ፡ ከዚያ ፡ ልጆች ፡ ቢኖሩት ፡ ከሥራው ፡ (ሠርቶ ፡ ካገኘው) በቀር ፡ ለእርሱ ፡ አይሁን ። ገንዘቡ ፡ ግን ፡ ለልጆች ፡ ተጠብቆ ፡ ይኑር ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ለሰው የው ፡ ከገንዘብ ፡ ወገን ፡ ያለውን ፡ እኛ ፡ ለልጆች ፡ እንሰጣለን ። ከሠርግ ፡ የቀደመው ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ግን ፡ ልጆች ፡ ከሌሉ ፡ ለሴቷ ፡ እንዲ

አንቀጽ ፡ ፳፱ ።

፱፻፶፭ ወዳግምስ ፡ ዘይደሉ ፡ በእንተ ፡ ዘማዊት ፡ ብእሲት ። ጠስ ፡ ፲ወ፩ዱ ፡ ወከማሁ ፡ ለእመ ፡ ስትየት ፡ ብእሲት ፡ ዘእንበለ ፡ ምክረ ፡ ምታ ፡ ምስለ ፡ ብእሲ ፡ ካልእ ፡ አው ፡ ተሐፅበት ፡ አው ፡ ስሐቀት ፡ አው ፡ ሖረት ፡ ኀበ ፡ መካነ ፡ አሥግሮ ፡ ወጉባኤ ፡ እንዘ ፡ ኢሀሎ ፡ ምታ ፡ አምነ ፡ ዝንቱ ። አው ፡ ኀደረት ፡ አፍአ ፡ እምቤታ ፡ ኀበ ፡ ካልእ ፡ ቤት ፡ ለእመ ፡ ኢኮነ ፡ በይቶታ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ አቡሃ ፡ ወለእመኒ ፡ አልባቲ ፡ አብ ፡ ወኮነ ፡ ዝንቱ ፡ ምክንያተ ፡ ኀዲሮታ ፡ በአፍአ ። ወበዘይከውን ፡ ከዋኔ ፡ ዝንቱ ፡ ሥርዓተ ፡ ተዋስቦታት ፡ እለ ፡ ውጉዛት ፡ ውስተ ፡ አክፋል ፡ ቀዳማውያን ። ረስጣ ፡ ፲ወ፬ቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ፭ቱ ፡ ወ፮ቱ ፡ ወናሁ ፡ ሀሎ ፡ ውስተ ፡ ካልእ ፡ እምውእቱ ፡ ኵልቈ ፡ ቀኖና ፡ ወያእቲ ፡ ረስጣ ፡ ዘ፲ወ፮ቱ ፡ ቀጠጅ ፡ ዘ፪ቱ ፡ በስ ፡ ፳ወ፭ቱ ፡ ዘ፵ወ፬ቱ ፡ ወዘተርፈሂ ፡ ዘተአምረ ፡ በዘከሮ ፡ በተባዕት ፡ ይትኌለቍ ፡ ላዕለ ፡ ዘተዐውቀ ፡ አስመ ፡ ውእቱ ፡ ዘከማሁ ።

፱፻፶፮ ወኀልስ ፡ በእንተ ፡ ሶበ ፡ ፈቀደ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ እማስኖተ ፡ ሕይወት ፡ ካልኡ ፡ ወእማስኖተ ፡ ንጽሓ ፡ ለብእሲት ። ጠስ ፡ ፲ወ፩ዱ ፡ ወእመ ፡ ብእሲት ፡ መከረት ፡ ለአኅጉሎ ፡ ሕይወተ ፡ ምታ ፡ በምንትኒ ፡ ግጽ ፡ እምግጻት ፡ አው ፡ አእመረት ፡ ከመ ፡ ካልአን ፡ ይጽሕቱ ፡ በዝንቱ ፡ ወኢከሠተት ፡ ሎቱ ። ኒቅያ ፡ ፱ወ፭ቱ ፡ ወዘአውሰበ ፡ ብእሲተ ፡ ወኮነ ፡ ማእከሌሆሙ ፡ ወማእከለ ፡ ብእሲት ፡ አከይ ፡ አው ፡ ምክንያት ፡ አምክንያታት ፡ ወኮነት ፡ ይእቲ ፡ በማሕተ ፡ ሎቱ ፡ ይትዐገሥ ፡ ኪያሃ ፡ ወይምሐክ ፡ ላቲ ፡ እስከ ፡ ትትመየጥ ፡ እምግብራ ፡ ኀበ ፡ ሠናይት ። ወለእመ ፡ ኢተከሀለ ፡ በዝንቱ ፡ ወተወስከ ፡ ግብራ ፡ ላዕሌሁ ፡ ያብጽሖ ፡ ኀበ ፡ ቀሲስ ፡ ዐቢይ ፡ አምቀሲሳን ፡ ወይኩን ፡ በሬቱ ፡ ማእከሌሆሙ ፡ ወለእመ ፡ አበየት ፡ ኪያሁ ፡ ስይፍታሕ ፡ ማእከሌሆሙ ፡ ኤጲስቆጶስ ። ወለእመ ፡ ኢተአዘዘት ፡ ሎቱኒ ፡ ወኀየት ፡ እምታ ፡ ወደግብእ ፡ ካዕበ ፡ ወእመስ ፡ ጸንዐት ፡ ወኢሰምዐት ፡ ቃሎ ፡ ለገቢእ ፡ ወይንግፍ ፡ እግእኒሁ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወጸበለ ፡ እገሪሁ ፡ ውስተ ፡ ዶዶሃ ። ወብውሕ ፡ ለብእሲሃ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ዘአፍ

ስለ ፡ ጋብቻ ።

ሆን ፡ እናዝዛለን ። የገንዘቡ ፡ ትርፍም ፡ በመካከል ፡ ይሁን ።

፱፻፶፭ ሁለተኛውም ፡ ስለአመንዝራዪቱ ፡ ሴት ፡ የሚገባውን ፡ ይናገራል ። ጠስ ፡ ፲፩ ። እንደዚሁም ፡ ሴት ፡ ያለባልዋ ፡ ፈቃድ ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ብትጠጣ ፡ ወይም ፡ ፍል ፡ ውሀ ፡ ብትታጠብ ፡ ወይም ፡ ብትስቅ ፡ ወይም ፡ ወደማጥመጃያና ፡ ወደስብሰባ ፡ ቦታ ፡ ከዚያ ፡ ባሏ ፡ ሳይኖር ፡ ብትሄድ ፡ ወይም ፡ ከቤቷ ፡ ውጭ ፡ በሌላ ፡ ቤት ፡ ብታድር ፡ ማደሯም ፡ በእባቷ ፡ ቤት ፡ ባይሆን ፡ አባት ፡ ባይኖራትም ፡ በውጭ ፡ የማደሯ ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፡ ቢሆን ፡ የዚህ ፡ ሁኔታ ፡ በመጀመሪያዎቹ ፡ ክፍሎች ፡ ውስጥ ፡ በተከለከሉት ፡ የጋብቻዎች ፡ ሥርዐት ፡ በሚሆን ፡ ገንዘብ ፡ ነው ። ረስጣ ፡ ፲፬ ። ከ፭ኛውና ፡ ከ፮ኛው ፡ በቀር ፡ እነሆ ፡ ከዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ወጥቶ ፡ በሌላ ፡ ውስጥ ፡ አለ ። ይህችውም ፡ ረስጣ ፡ ፲፮ ። ቀጠጅ ፡ ፪ ። በስ ፡ ፳፭ ። ፵፬ ፡ ነው ። በወንድ ፡ ላይ ፡ በመነገር ፡ ታውቆ ፡ የቀረውም ፡ በታወቀው ፡ ላይ ፡ ይቆጠራል ። እርሱ ፡ እንደ ፡ እርሱ ፡ ነውና ።

፱፻፶፮ ፫ኛውም ፡ ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ ያንዱን ፡ ሕይወት ፡ ሊያጠፋ ፡ የሚስቱንም ፡ ንጽሕና ፡ ሊያሳድፍ ፡ በወደደ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚሆነው ፡ ይናገራል ። ጠስ ፡ ፲፩ ። ሚስት ፡ ከሥራ ፡ በማናቸውም ፡ ሥራ ፡ የባሏን ፡ ሕይወት ፡ ለማጥፋት ፡ ብትመክር ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ሲመክሩ ፡ አውቃ ፡ ባትገልጽለት ፡ ነው ። ኒቅያ ፡ ፶፭ ። ሚስት ፡ ያገባ ፡ ሰው ፡ በእርሱና ፡ በሚስቱ ፡ መካከል ፡ ፀብ ፡ ክርክር ፡ ቢኖር ፡ ወይም ፡ ከምክንያቶች ፡ ወገን ፡ ምክንያት ፡ ቢኖር ፡ እርሱን ፡ የምትበድለው ፡ ብትሆን ፡ ከክፉ ፡ ሥራዋ ፡ ወደበጎ ፡ ሥራ ፡ እስክትመለስ ፡ ድረስ ፡ ይታገሣት ፡ ይራራላት ። በዚህ ፡ ባይቻል ፡ ክፋቷ ፡ በዚያው ፡ ላይ ፡ ቢጨመር ፡ ከቀሳውስት ፡ ወገን ፡ ወደ ፡ ትልቁ ፡ ቄስ ፡ ያድርሳት ። በመካከላቸውም ፡ አስታራቂ ፡ ይሁን ። እርሱን ፡ እንቢ ፡ ብትል ፡ ኤጲስቆጶሱ ፡ በመካከላቸው ፡ ይፍረድ ። ለእርሱም ፡ ባትታዘዝ ፡ ከባሏም ፡ ብትሸሽ ፡ ዳግመኛ ፡ ይመልሳት ። ብትፀና ፡ ግን ፡ ለመመለስም ፡ ቃሉን ፡ ባትሰማ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ከደጅዋ ፡ ጫማውንና ፡ የእግሩን ፡ ትቢያ ፡ ያራግፍ ። ለባሏ ፡ የወደደውን ፡ ሊያደርግ ፡ ሥልጣን ፡ እሰው ።

ቀረ ፡ እመኒ ፡ ፈቀደ ፡ አውስቦ ፡ ለያውስብ ፡ ወለእመ ፡ ፈተወ ፡ ከመ ፡ ይንበር ፡ ላዕለ ፡ ማብሩ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ሎቱ ፡ ትዕግሥት ፡ ይንበር ፡ ወእመ ፡ ኮነ ፡ ውናየ ፡ ይመንኩስ ።

፬፻፵፯ ወለእመ ፡ ተሀውቀ ፡ እምግብሩ ፡ ከመ ፡ ለሊሁ ፡ ገፋዒሃ ፡ ውእቱ ፡ ላቲ ፡ ወጸላኢሃ ፡ ወይፈቅድ ፡ አቅሞቶ ፡ እከዩ ፡ ላዕሌሃ ፡ ከመ ፡ ይትፈለጣ ፡ ኢይትወከፉ ፡ እምኔሁ ፡ ዘንተ ፡ እላ ፡ ያገብርዎ ፡ ከመ ፡ ይንበር ፡ ምስሌሃ ። ወለእመ ፡ አበየ ፡ ውእቱ ፡ ወአፍቀረ ፡ ተፈልጦታ ፡ እማኅደሩ ፡ ይትከላእ ፡ እምቍርባን ፡ ወእምበዊአ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

፬፻፵፰ ሥርዋጽ ፡ ፳ወ፪ቱ ፡ ዝንቱ ፡ ዘኢተአዘዘ ፡ ቦቱ ፡ በውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወነበረ ፡ ከመ ፡ ይትዐወቅ ፡ ባሕቲቱ ።

፬፻፵፱ ጠስ ፡ ፲ወ፩፮ ፡ ወምክንያትሰ ፡ ዘይደልዋ ፡ ለብእሲት ፡ እምክንያት ፡ ከሡት ፡ ከመ ፡ ትሣእ ፡ እምቤተ ፡ ምታ ፡ ወዘይመስሎ ፡ ለዝንቱ ፡ ለእመ ፡ ተጓጕለወ ፡ ብእሲ ፡ ለአማስኖ ፡ ሕይወተ ፡ ብእሲቱ ፡ በምንትኒ ፡ ገጽ ፡ እምገጸት ፡ አው ፡ ካልአን ፡ መከሩ ፡ ዘንተ ፡ ላዕሌሃ ፡ ወአእመርሙ ፡ ወኢነገሩ ። አው ፡ እመኒ ፡ ተጓጕለወ ፡ ላዕለ ፡ ንጽሐ ፡ ዚአሃ ፡ ወመጠዋ ፡ ለዘይዜሙ ፡ ባቲ ፡ ወለእመ ፡ ኮኑ ፡ ሰምዐ ፡ ላዕሌሁ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ አስተጸንዐ ፡ ላዕሌሃ ፡ ዝሙተ ። ወኢተክሀሎ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ዘንተ ፡ በገሃድ ፡ ፍሁ ፡ ተበውሐ ፡ ላቲ ፡ በዛቲ ፡ ምክንያት ፡ ከመ ፡ ትትፈለጥ ፡ እምኔሁ ፡ ወትንሣእ ፡ ትሎታ ፡ ወይወስከዋ ፡ እምኅሃ ፡ ዘቀደመ ፡ እመርዓ ።

፬፻፶ ሥርዋጽ ፡ ፳ወ፫ቱ ፡ ዝንቱስ ፡ ዘኢይገብርዎ ፡ ሎቱ ፡ ወትንሣእ ፡ ካዕበ ፡ እምኅሪቱ ፡ ዘተርፈ ። ወለእመ ፡ እልባቲ ፡ ውሉድ ፡ በአምሳነ ፡ ማል ሰተ ፡ እደዊሃ ፡ ለእምኃ ፡ ዘቀደመት ፡ እመርዓ ፡ ወእመሰ ፡ ባቲ ፡ ውሉድ ፡ እምኔሁ ፡ ንሕነ ፡ ንኤዝዝ ፡ ከመ ፡ ይትዐቀብ ፡ ኮሉ ፡ ንዋዩ ፡ ለውሉዶሙ ፡ እምነ ፡ ዘተርፈ ፡ ወዘአዘዝነ ፡ ንሚእ ፡ እምኃ ፡ ዘተደመት ፡ እመርዓ ።

፬፻፶፩ ሥርዋጽ ፡ ፳ወ፬ቱ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይጸናዕ ፡ ኮንኑ ፡ ዝሙታ ፡ ለብእሲት ፡ ሬድፋደ ፡ እምብእሲሃ ፡ ወዝንቱሰ ፡ ዘተገብረ ፡ እስመ ፡ ዝሙትስ ፡ ለብእሲ ፡ ዝኒ ፡ በእንተ ፡ ከመ ፡ ኢመፍትው ፡ ትትፈለጥ ፡ ብእሲት ፡ እምኔሁ ፡ እስመ ፡ ብዙኅ፡



ሊያገባ ፡ ቢወድ ፡ ያግባ ፡ በንጽሕና ፡ ሊኖር ፡ ቢወድ ፡ ትእግሥትም ፡ ቢኖረው ፡ ይኑር ። መልኩም ፡ ከሆነም ፡ ይመንኩስ ።

፬፻፵፯ ከሥራው ፡ የተነሣ ፡ እርሱ ፡ እርሷን ፡ የሚበድላት ፡ ጠላቷ ፡ እንደሆነ ፡ ቢታወቅ ፡ ከእርሷም ፡ ይለይ ፡ ዘንድ ፡ በእርሷ ፡ ላይ ፡ ክፉት ፡ ማድረግን ፡ ቢወድ ፡ ይህን ፡ በእርሱ ፡ አይቀበሉ ። ከእርሷ ፡ ጋራ ፡ እንዲኖር ፡ ግድ ፡ ይበሉት ፡ እንጂ ። እርሱ ፡ ከቤቱ ፡ እንድትወጣለት ፡ ወዶ ፡ እንቢ ፡ ቢል ፡ ከቍርባንና ፡ ወደቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከመግባት ፡ ይከልከል ።

፬፻፵፰ ሥርዋጽ ፡ ፳፪ ። ይህ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያናችን ፡ ውስጥ ፡ ያልታዘዘበት ፡ ነው ። ይታወቅ ፡ ዘንድ ፡ ብቻ ፡ ተጻፈ ፡ እንጂ ።

፬፻፵፱ ጠስ ፡ ፲፩ ። ከባሏ ፡ ቤት ፡ ትወጣ ፡ ዘንድ ፡ ይህንም ፡ የመሰለውን ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ ከታወቀ ፡ ምክንያት ፡ ወገን ፡ ከሴት ፡ የሚገባት ፡ ምክንያትስ ፡ ከሥራ ፡ በማናቸውም ፡ ሥራ ፡ ባል ፡ የሚስቱን ፡ ሕይወት ፡ ለማጥፋት ፡ ቢተነኮል ፡ ነው ። ወይም ፡ ሌሎች ፡ ይህን ፡ በእርሷ ፡ ላይ ፡ እንደመከሩ ፡ አውቆ ፡ ባይነግራት ፡ ወይም ፡ በንጽሕናዋ ፡ ላይ ፡ ተተንኰሎ ፡ ዝሙት ፡ ለሚሠራባት ፡ ሰው ፡ አሳልፎ ፡ ቢሰጣት ፡ ነው ። እርሱ ፡ በእርሷ ፡ ላይ ፡ ዝሙትን ፡ እንዳጸናባት ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ቢመሰክሩ ፡ ይህን ፡ በግልጽ ፡ ሊያደርግ ፡ ባይቻለው ፡ እነሆ ፡ በዚች ፡ ምክንያት ፡ ከእርሱ ፡ ትለይ ፡ ዘንድ ፡ ተፈቀደላት ። ትልወቷንም ፡ ትውሰድ ። ከሠርግ ፡ የቀደመ ፡ እጅ ፡ መንሻውንም ፡ ይጨምሩላት ።

፬፻፶ ሥርዋጽ ፡ ፳፫ ። ይህስ ፡ የማያደርጉት ፡ ነው ። ደግመኛ ፡ ከቀረው ፡ ገንዘብ ፡ ትውሰድ ። ልጅ ፡ ባይኖራት ፡ ከሠርግ ፡ ከቀደመው ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ምስቱን ፡ እጅ ፡ ያህል ፡ ትውሰድ ። ከእርሱ ፡ ልጆች ፡ ቢኖሯት ፡ ግን ፡ ከቀረውና ፡ ከሠርግ ፡ ከቀደመችው ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ እንድትወስድ ፡ ካዘዝነው ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ ለልጆቻቸው ፡ ይጠበቅ ፡ ዘንድ ፡ እኛ ፡ እናዝዛለን ።

፬፻፶፩ ሥርዋጽ ፡ ፳፬ ። ከባሏ ፡ ይልቅ ፡ የሴት ፡ የዝሙቷ ፡ ቅጣት ፡ ሊጸና ፡ ይገባል ። ይህም ፡ የተደረገ ፡ ሴት ፡ ከእርሱ ፡ ትለይ ፡ ዘንድ ፡ ስለማይገባ ፡ የወንድ ፡ ዝሙት ፡ ይህ ፡ ነውና ። የሕግ ፡ ብዙ ፡ ፍላጎቱ ፡ በስምች ፡ ላይ ፡ በየራሳቸው ፡

አንቀጽ ፡ ፳፱ ።

ኀሡሣሁ ፡ ለሕግ ፡ ከመ ፡ ያእትት ፡ ለጸብ ፡ ዘይመጽእ ፡ ላዕለ ፡ ሰብእ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ወለ ብእሲሰ ፡ ፈድፋደ ፡ ይእኅዞ ፡ ቅንአት ፡ እስከ ፡ ይቀትል ፡ ብእሲቶ ፡ ለእመ ፡ ዘመወት ፡ ላዕሌሁ ወዓዲ ፡ ይቀትል ፡ ብእሴ ፡ ዘዘመወ ፡ ምስሌሃ ወዓዲ ይገብር ፡ ዘንተ ፡ በአበሃ ፡ አው ፡ በእ ኁሃ ፡ አው ፡ በእማ ፡ ወብእሲትስ ፡ ወአዝማ ዲሃ ፡ አኮ ፡ ከማሁ ። ወዓዲ ፡ እስመ ዘርአ ይቀውም ፡ በእንተ ፡ ተበቀሎተ ፡ ብእሲት ፡ ወለ እመ ፡ ዘመወት ፡ ይእቲ ፡ ይማስን ፡ ርስት ፡ ወት ውልደ ፡ አበው ። ወዓዲ ፡ እስመ ፡ ድንግል በዝሙት ፡ ተማስን ፡ አርአያ ፡ ድንግልናሃ ፡ ወብእሲስ ፡ አኮ ፡ ከማሁ ።

፱፻፳፱ በሕገጋትስ ካልአት ሀለወ ተማግጾ ዙንቱ ፡ በብእሲ ፡ በእንተ ፡ ዘዘከረ ፡ ነውረ ፡ ላዕለ ብእሲቱ ፡ ወበእንተ ፡ ዘኢያዖቀ ፡ ዘሐሰየ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ባቲ ፡ ሶበ ፡ ተመውሀት ለእለ ይኬ ውኑ ፡ ስምዐ ፡ በላዕሌሃ ። ወለእመ ተረክበ ብእሲ ምስለ ካልእት ብእሲት በውስተ ማኅደሩ በዮነደር ቦቱ ፡ ምስለ ፡ ብእሲቱ ፡ አው ተደመረ በውስቴ ሀገር ምስለ ካል እት ብእሲት ወዘለፍዎ ፡ በእንተ ፡ ሀቤተ ምስሌሃ ብዙኀ ጊዜያተ ወተነግረ ውዳሴ በልሳን ወላድያኒሁ ወወላድያኒሃ ለብእ ሲት ፡ አው በአፈ ካልእን ሰማዕት እምእ መናን ፡ ወኢኀደገ ፡ ሐሰተ ፡ ይትኀደግ ፡ አው ስሀ ወትኅሥእ ትሎቱ ዘእምጽአቶ ኀቤሁ ወእም፡ኀ ዘቀደመ እምከብካብ ፡ ወትሥለ ስቲ እድ እምንዋየ ብእሲ ትንሣእ ። ወእ መሰ ሳቲ ውሉድ እምኔሁ ለትግበር ብእ ሲት ፡ ዘንተ ፡ ግብረ ፡ ዘሂ ፡ ረከበት ፡ እምነ ፡ አም፡ኀ እንተ ተደመት እመርዓ ። ወሥለ ስተ ፡ እድ ፡ እምጥሪተ ፡ ብእሲ ፡ ዘተገሠጸ ፡ ትንሣእ ፡ ወዘሂ ፡ ይመልክ ፡ ኪያሁ ፡ ይትዐቀብ ፡ ለውሉዶሙ ። ወሰእመሰ ፡ አልቦቱ ፡ ውሉድ ፡ ንሕነ ንኤዝዝ ከመ ይኩን ላቲ ምልክ ናሁ ለዝንቱ ንዋይ ።

፱፻፴ ወበእንተ ተፈልጦቱ ብእሲ እምብእሲቱ ሀሎ ካልእ ቀኖና ውእቱ ዘይደሉ ወቦቱ ይግበሩ ። መጅ ፡ ፳ወ፬ቱ ፡ ወለሀማውያንሰ ፡ ኢይፍልጡ ፡ ሚእከሌሆሙ ፡ ወማእከለ ፡ አንስ ቲያሆሙ ። ወከማሁ ፡ ዘእስተዋዳያ ፡ ለብእ ሲቱ ፡ በዘኢይመውዓ ፡ እስመ ፡ እምነ ፡

ስለ ፡ ጋብቻ ።

የመጣውን ፡ ጭንቅ ፡ ያርቅ ፡ ዘንድ ነው እኮ ። ይልቁንም ፡ ወንድ ፡ ግን ፡ በእርሱ ላይ ብትስስንበት ፡ ሚስቱን ፡ እስኪገድል ድረስ ቅንዓት ፡ ይይዘዋል ። ዳግመኛም ፡ ከእርሷ ጋራ ፡ የሰሰነውን ፡ ወንድ ፡ ይገድላል ። ዳግመኛም ይህን ፡ ባባቷ ፡ ወይም ፡ በወንድሟ ፡ ወይም በእናቷ ፡ ያደርጋል ። ሴቲና ፡ ዘመዶቿ ግን እንዲህ ፡ አይደሉም ። ዳግመኛም ፡ ስለሴት መጠበቅ ፡ ዘር ፡ ይተካልና ፡ እርሷ ፡ ብትስስን ርስት ፡ የአበው ፡ ትውልድ ፡ ይጠፋል ። ዳግመ ኛም ፡ ድንግል ፡ በዝሙት ፡ ማኅተመ ፡ ድንግ ልናዋን ፡ ታጠፋለችና ። ወንድ ፡ ግን ፡ እንዲህ አይደለም ።

፱፻፳፱ በሌሎች ፡ መጻሕፍት ፡ ግን ፡ በሚስቱ ፡ ላይ ፡ ነውር ፡ ስለተናገረና ፡ በተቸነፈች ፡ ጊዜ ፡ በእ ርሷ ፡ ላይ ፡ ምስክር ፡ ለሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ያደር ግባት ፡ ዘንድ ፡ ያሰበውን ፡ ስላልገለጠ ፡ በወ ንድ ፡ የፍርድ ፡ ቅጣት ፡ አለ ። ወንድ ፡ ከሚ ስቱ ፡ ጋራ ፡ በሚያድርበት ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ከሌላ ፡ ሴት ፡ ጋራ ፡ ቢገኝ ፡ ወይም ፡ በሀገር ፡ ከሌላ ፡ ሴት ፡ ጋራ ፡ ቢገናኝ ፡ ከእርሷ ፡ ጋራ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ስለማደሩ ፡ ቢዘልፉት ፡ ነገረ ፡ ሥራ ንቱ ፡ በወላጆቹና ፡ በሴትዋ ፡ ወላጆች ፡ አን ደበት ፡ ወይም ፡ ከምእመናን ፡ ወገን ፡ በሌሎች፡ ምስክሮች ፡ አፍ ፡ ቢነገር ፡ ሐሰቱን ፡ ባይተው ፡ ጋብቻ ፡ ይፈርሳል ። ወደእርሱ ፡ ያመጣችውን ፡ ትልወት ፡ ትውሰድ ፡ ከሥርግ ፡ የቀደመ ፡ እጅ ፡ መንሻውንና ፡ ከሰውየው ፡ ገንዘብ ፡ ሦስቱን ፡ እጅ ፡ ትውሰድ ። ከእርሱ ፡ ልጆች ፡ ቢኖሯት ፡ ግን ፡ ሴትየዋ ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ ታድርግ ። ከሠ ርግ ፡ ከቀደመችው ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ያገኘችው ንና ፡ ከተቀጣው ፡ ከባሏ ፡ ገንዘብ ፡ ሦስት ፡ እጅ ትውሰድ ። የተገዛውም ፡ ለልጆቻቸው ፡ ይጠ በቅ ። ልጆች ፡ ባይኖሩት ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ገንዘብ፡ ማዘዝ ፡ ለእርሷ ፡ እንዲሆን ፡ እኛ ፡ እናዝዛለን ።

፱፻፴ ባልን ፡ ከሚስቱ ፡ ስለመለየት ፡ ሌላ ፡ ሕግ ፡ አለ ፡ ይኸውም ፡ ሊሠሩበት ፡ የሚገባ ፡ ነው ። መጅ ፡ ፳፬ ። ለአመንዝራዎች ፡ ግን ፡ በእነርሱ፡ መካከልና ፡ በሚስቶቻቸው ፡ መካከል ፡ አይ ለዩ ። በማይረታበት ፡ ነገር ፡ ሚስቱን ፡ የሚከ ስም ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። ከነገር ፡ ሥራ ፡ ወገን ፡

አንቀጽ ፡ ፳፰ ።

ውዴት ፡ ዘይከውን ፡ እሙነ ፡ ወኢይጸንዕ ፡ ጥያቄሁ ። ዝንቱኒ ፡ ወዘይመስሎ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ የሀቡ ፡ በእንቲአሁ ፡ ኵነኔ ፡ ንስሓ ፡ እለ ፡ ቦሙ ፡ ሥልጣን ፡ ላዕለ ፡ ሥርየተ ፡ ኃጢአት ፡ ወእኮ ፡ ከመ ፡ ይፍልጡ ፡ ብእሲተ ፡ እም ብእሲሃ ።

ዕቍባትን ፡ ስለመከልከል ።

እውነት ፡ የሚሆንና ፡ እርግጠኛነቱ ፡ የማይፀና ፡ አለና ፡ በዚህና ፡ በመሰለው ፡ ሴትን ፡ ከባልዋ ፡ ለመለየት ፡ ያይደለ ፡ ኃጢአትን ፡ ለማስተሥረይ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ ስለእርሱ ፡ የንስሐ ፡ ቅጣት ሊሰጡ ፡ ይገባል ።

## አንቀጽ ፳ወ፩ቱ ።

በእንተ ፡ አኀርሞተ ፡ ዕቁባት ፡ ወግብረ ፡ ዕቁ ባት ፡ ወብእሲት ፡ ዘእስርት ፡ በሕግ ።

፱፻፳፬ ነገሩ ፡ ዕቅብትሰ ፡ በውስተ ፡ ሕግነ ፡ ቅድስት ፡ ሕሩም ፡ ውእቱ ፡ እስመ ፡ ውዑእ ፡ ውእቱ ፡ እም አውስቦ ፡ ዘብዉሕ ፡ እምቀዳሚ፡ ዘተጠየቀ ፡ ውእቱኒ ፡ ዝሙት ፡ ዘዘልፍ።

፱፻፳፭ ረስጠብ ፡ ፳ወ፩ቱ ፡ እመቦ ፡ ዘቦቱ ፡ ዕቅብት ፡ እመ ፡ ኮነት ፡ አመተ ፡ ዚአሁ ፡ ለይኅድግ ፡ ወያ ውስብ ፡ በከመ ፡ ሕግ ፡ ወእመሰ ፡ ኮነት ፡ አግዓ ዚተ ፡ ለያውስባ ፡ በከመ ፡ ሕግ ። ወለእመ ፡ ኢፈ ቀደ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ዘንተ ፡ ይሰደድ ።

፱፻፳፮ ጠስ ፡ ፩ቱ ፡ ወኢይኩን ፡ ለፅዱሂ ፡ መባሕት ፡ ከመ ፡ ይንበር ፡ ምስለ ፡ ዕቅብት ፡ ውስተ ፡ ማኅ ደሩ ፡ ወአልቦቱ ፡ ፍልጠት ፡ ማእከሌሁ ፡ ወማ እከለ ፡ ዘማውያን ፡ ወእመ ፡ ፈቀደ ፡ ተሳትፎታ ለያውስባ ፡ በሥርዓተ ፡ ሰብሳብ ፡ ዘሕግ ። ወለእ መሰ ፡ ይሬኢ ፡ ከመ ፡ ይእቲ ፡ ኢኮነት ፡ ድሉተ ከመ ፡ ትስመይ ፡ ሎቱ ፡ ብእሲተ ፡ ሕግ ፡ ለይስ ድዳ ፡ ወይንግእ ፡ ዘየንቱሃ ፡ ዘትግኅንዮ ፡ ወለ እመኒ ፡ ፈቀደ ፡ ለይንበር ፡ በንጽሕ ።

፱፻፳፯ ዘ፴ወ፱ቱ ፡ ወዘሎቱ ፡ ብእሲት ፡ ወዘያወስብ ፡ አመተ ፡ ዚአሁ ፡ ይትገሠጽ ፡ ወይደልዎ ፡ ለሊቅ ፡ ከመ ፡ ይሢጥ ፡ ኪያሃ ፡ ውስተ ፡ ካልእ ፡ ብሔር ፡ ርኁቅ ።

፱፻፳፰ ረስጠብ ፡ ፳ወ፱ቱ ፡ ፳ወ፩ቱ ፡ ወዕቅብቱ ፡ ዘኢ ማእምንት ፡ ለዘኢየአምን ፡ ወሰበ ፡ ኮነት አመተ ፡ ዚአሁ ፡ ዘእረኵሰት ፡ ምስለ ፡ ካልእ ፡ ወአልኅተት ፡ ውሉዳ ፡ ለትባእ ፡ ወእመሰ ረኵሰት ፡ ምስለ ፡ ካልእን ፡ ለትሰደድ ።

፱፻፳፱ በስ ፡ ፯ቱ ፡ ወኢይደልዎ ፡ ለብእሲ ፡ ከመ ፡ ያን ብር ፡ ሎቱ ፡ ዕቅብተ ፡ እምድኅረ ፡ አስመ ፡ እግ ዚእነ ፡ ክርስቶስ ፡ ሠርዐ ፡ ሕገ ፡ ግዕዛን ።

## አንቀጽ ፡ ፳፩ ።

ዕቁባት ፡ ማኖርን ፡ ስለመከልከል ፡ ስለዕቁባት፡ ሥራ ፡ በሕግ ፡ ስለታሠረችም ፡ ሴት ፡ ይናገ ራል ።

፱፻፳፬ ዕቁባት ፡ ማኖርስ ፡ በተቀደሰች ፡ ሕጋችን ፡ ውስጥ ፡ የተከለከለ ፡ ነው ። ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ከተረዳው ፡ ከሚገባው ፡ ጋብቻ ፡ የወጣ ፡ ነውና። ይኸውም ፡ የዘወትር ፡ ዝሙት ፡ ነው ።

፱፻፳፭ ረስጠብ ፡ ፳፩ ። ዕቁባት ፡ ያለችው ፡ ሰው ፡ ቢኖ ር ፡ አገልጋዩ ፡ ብትሆን ፡ ይተውና ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፡ ያግባ ። ነፃ ፡ የወጣች ፡ ብትሆን ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፡ ያግባት ። ይህን ፡ ሊያደርግ ፡ ባይ ወድ ፡ ይለይ ።

፱፻፳፮ ጠስ ፡ ፩ ። አንድ ፡ ሰውስ ፡ እንኳ ፡ በቤቱ ፡ ከዕ ቁባት ፡ ጋራ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣን ፡ አይኑ ረው ። በእርሱና ፡ በዘማውያን ፡ መካከል ፡ ልዩ ነት ፡ የለም ። ሊያገባት ፡ ቢወድ ፡ በሕግ ፡ ጋብቻ ፡ ሥርዓት ፡ ያግባት ። ለእርሱ ፡ የሕግ ፡ ሚስት ፡ ለመባል ፡ የተገባች ፡ እንዳልሆነች ፡ ቢያውቅ ፡ ግን ፡ ይፍታት ፡ በእርሷ ፡ ፈንታ ፡ የተሻለችውን ፡ ያግባ ። ቢወድም ፡ በንጽሕና ፡ ይኑር ።

፱፻፳፯ ፴፱ ። ሚስት ፡ እያለችው ፡ ከአገልጋዩ ፡ የሚ ደርስ ፡ ይቀጣ ። ለዳኛ ፡ ወደሌላ ፡ ሩቅ ፡ ሀገር ፡ እርሷን ፡ ሊሸጥ ፡ ይገባዋል ።

፱፻፳፰ ረስጠብ ፡ ፳፱ ። ፳፩ ። ላላመነው ፡ ያላመነች ፡ ዕቁባት ፡ ከሌላ ፡ ጋር ፡ ያልረከሰች ፡ አገልጋዩ ፡ ብትሆን ፡ ልጆቹንም ፡ ያሳደገች ፡ ከሆነች ፡ ትግባ ፡ (ትጠመቅ) ፡ ከሌሎች ፡ ጋራ ፡ የረከሰች፡ ብትሆን ፡ ግን ፡ ትለይ ።

፱፻፳፱ በስ ፡ ፯ ። ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ ዕቁባት ፡ ሊያኖር ፡ ለሰው ፡ አይገባውም ። ጌታችን ፡ ክርስቶስ ፡ የነፃነት ፡ ሕግ ፡ ሠርቷልና ። ለዳዊት ፡ ለሰሎሞ

አንቀጽ ፡ ፳፮ ።

ወኢመ ትቢ ፡ ከመ ፡ ለዳዊት ፡ ወለሰሎሞን ወለካልእን ፡ ከና ፡ ሎሙ ፡ ዕቅብታተ ፡ እመሰ ፈቀድከ ፡ ከመ ፡ ታእምር ስማዕኪ ፡ እስመ ፡ በውእቱ ፡ ዘመን ፡ ኮኑ ፡ ሰብእ ፡ ሙኑዳን ፡ በዲበ ፡ ምድር ። በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ተበውሐ ፡ ሎሙ ፡ ከመ ፡ ያውስቡ ፡ ወያንብሩ ፡ ሎሙ ፡ ዕቅብታተ ፡ ከመ ፡ ይብዝኑ ፡ ሰብእ ፡ በዲበ ምድር ። ወሶበ ፡ ርእየ ፡ ከመ ፡ ምድር ፡ መልእት ፡ ከልአ ፡ ሕግ ፡ እምንግእ ፡ ዕቅብት ፡ ወአንበረ ፡ ሕገ ፡ እውሰቦ ።

ስለ ፡ ስጦታ ፡ (ሀብት)

ን ፡ ለሌሎችም ፡ ዕቁባት ፡ ነበሩቸውሳ ፡ ብትል፡ ልታውቅ ፡ ከወደድኽ ፡ ስማ ! በዚያ ፡ ዘመን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ሰዎች ፡ ጥቂቶች ፡ ስለነበሩ ፡ ሰዎች ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ይበዙ ፡ ዘንድ ፡ ስለዚህ፡ ሚስት ፡ እንዲያገቡ ፡ ዕቁባት ፡ እንዲኖሩ ፡ ተፈቀደላቸው ። ምድር ፡ እንደመላች ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ዕቁባትን ፡ ከማኖር ፡ ከልክሎ ፡ ሚስት ፡ የማግባትን ፡ ሕግ ፡ ሠራ ።

## አንቀጽ ፡ ፳ወ፯ቱ ።

በእንተ ፡ ሀብት ።

፱፻፸ ወመብዝኅቲሁ ፡ እመጽሐፈ ፡ ጠስ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ፲ወ፫ቱ ፡ በእንተ ፡ ሀብታት ፡ ወከዊነ ፡ ሀብታት፡ ውእቱ ፡ ያከውን ፡ እምኔሁ ፡ ገጸት ። ወውእቱ ፡ ሀብት ፡ ወወሀቢ ፡ መዘይሁብዎ ፡ ሎቱ ፡ ወንዋይኒ ፡ ዘይሁቡ ፡ ኪያሁ ፡ ወተረፈ ፡ ትእዛዝ ።

፱፻፸፩ ሀብትሰ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ የሀብዎሙ ፡ ለእለ ፡ ኢኮኑ ፡ ድልዋነ ፡ ለመጽውቶ ፡ ወምጽዋትኒ ፡ ትከውን ፡ ለዘይደልዎ ። ወሀብትሰ ፡ ምግባረ ፡ ትሩፋት ፡ ይእቲ ፡ ዘይደሉ ፡ ውሂቦታ ፡ እምድኅረ ፡ ምጽዋት ። ወእምከመ ፡ ወሀበ ፡ ወሃቢ ፡ ኪያሃ ፡ ወተወከፈ ፡ ዘይሁብዎ ፡ ሎቱ ፡ ንዋየ ፡ ዘትትወሀብ ፡ ወእምዝ ፡ ይደሉ ፡ ሎቱ ፡ ይኩን ፡ ላዕሌሁ ፡ ወይሥራዕ ፡ በቱ ፡ ከመ ፡ ወሀቢሁ ።

፱፻፸፪ ወለወሀቢኒ ፡ ኢትከውን ፡ እማነ ፡ እምኔሁ ፡ ሀብት ፡ ለእመ ፡ ኢኮነ ፡ ብጹሐ ፡ እምዓመ ፡ ወማእምረ ፡ ወእግዓዚ ፡ ወነሩየ ፡ በአልባቲ ፡ ፍርሃት ፡ እምዝወሀበ ። ወእመሰ ፡ ዘይፈርሆ ፡ እምዝ ፡ ወሀበ ፡ ኢይትፈጸም ፡ ሎቱ ፡ ወእመኒ ፡ ሞተ ፡ ወሀቢሁ ፡ ኢይግባእ ፡ እምኔሃ ፡ በስምዕ ውኩፍ ፡ ኢበጎቡእ ፡ ወኢ ፡ በከሠት ።

፱፻፸፫ ወለወሀቢሰ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ የሀብ ፡ በሕይወቱ ፡ እመ ፡ ፈቀደ ፡ በጊዜሁ ፡ ዘእንበለ ፡ ውሳኔ ዕድሜ ። ወለእመ ፡ ፈተደ ፡ እምድኅሬሁ ፡ በትእዛዝ ፡ ወበጊዜ ፡ እሙር ፡ ዘይመጽእ ፡ ወሎቱ ፡ ድልው ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ በጊዜ ፡ ሞቱ ፡ ተፍጻሜታ ፡ እምድኅረ ፡ ዕረፍቱ ።

## አንቀጽ ፡ ፳፯ ።

ስለ ፡ ስጦታ ፡ ይናገራል ።

፱፻፸ አብዛኛውም ፡ ከጠስ ፡ መጽሐፍ ፡ የተገኘ ፡ ነው ። ጠስ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ። ስለስጦታዎች ፡ ይናገራል ። የስጦታ ፡ ሁኔታ ፡ ከ፫ ፡ ወገን ፡ ነው ። እነዚህም ፡ ስጦታ ፡ ሰጪ ፡ ለእርሱ ፡ የሚሰጡት ሰው እርሱን ፡ የሚሰጡት ፡ ገንዘብ ፡ ከትእዛዝ ፡ የቀረውም ናቸው ።

፱፻፸፩ ስጦታስ ፡ ምጽዋት ፡ ለመስጠት ፡ ለማይችሉት፡ ሰዎች ፡ ሊሰጡአቸው ፡ ይገባል ። ምጽዋትም ፡ ለሚገባው ፡ ትሆናለች ። ስጦታስ ፡ ከምጽዋት ፡ ቀጥሎ ፡ ሊሰጧት ፡ የሚገባ ፡ የትሩፋት ፡ ሥራ ፡ ናት ። ሰጪ ፡ እርሷን ፡ ከሰጠ ፡ የምትሰጠዋንም ገንዘብ ፡ የሚሰጡት ፡ ሰው ፡ ከተቀበለ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንደሰጪው ፡ ይሠራበት ፡ ዘንድ ፡ በገንዘቡ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ሊኖረው ፡ ይገባል ።

፱፻፸፪ ሰጪውም ፡ እካለ ፡ መጠን ፡ ያደረሰ ፡ አዋቂ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ የተመረጠ ፡ ከሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ የተነጣ ፡ ፍርሃት ፡ የሌለበት ፡ ካልሆነ ፡ ስጦታው ፡ የታመነች ፡ አትሆንም ። ከሰጠ ፡ በኋላ ፡ የሚፈራ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ አይጸናለትም ። ሰጪው ቢሞትም ፡ በስውርም ፡ ቢሆን ፡ በግልጽ ፡ ስጦታው ፡ ተቀባይነት ፡ ባለው ፡ ምስክር ፡ ከተረጋገጠ ፡ አይመለስ ።

፱፻፸፫ ለሰጪ ፡ ግን ፡ በሕይወት ፡ ሳለ ፡ ዘመን ፡ ሳይወስን ፡ በጊዜው ፡ ሊሰጥ ፡ ቢወድ ፡ መስጠት ፡ ይገባዋል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በማዘዝና ፡ በሚመጣው በታወቀ ፡ ጊዜ ፡ ቢወድ ፡ ፍጻሜዋን ፡ በሞቱ ፡ ጊዜ ፡ ሊያደርግ ፡ ይገባዋል ።

አንቀጽ ፡ ፳፮ ።

ወእመ ትቤ ፡ ከመ ፡ ለዳዊት ፡ ወለሰሎሞን ወለካልእን ፡ ከና ፡ ሎሙ ፡ ዕቅብታት ፡ እመሰ ፈተድከ ፡ ከመ ፡ ታእምር ስማዕኬ ፡ እስመ ፡ በውእቱ ፡ ዘመን ፡ ኮኑ ፡ ሰብእ ፡ ውኁዳን ፡ በዲበ ፡ ምድር ። በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ተበውሐ ፡ ሎሙ ፡ ከመ ፡ ያውስቡ ፡ ወያንብሩ ፡ ሎሙ ፡ ዕቅብታት ፡ ከመ ፡ ይብዝኁ ፡ ሰብእ ፡ በዲበ ፡ ምድር ። ወሶበ ፡ ርእየ ፡ ከመ ፡ ምድር ፡ መልእት ፡ ከልአ ፡ ሕገ ፡ እምንሣእ ፡ ዕቅብት ፡ ወአንበረ ፡ ሕገ ፡ አውስቦ ።

ስለ ፡ ስጦታ ። (ሀብት)

ን ፡ ለሌሎችም ፡ ዕቁባት ፡ ነበሩዋቸውሳ ፡ ብትል ፡ ልታውቅ ፡ ከወደድህ ፡ ስማ ! በዚያ ፡ ዘመን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ሰዎች ፡ ጥቂቶች ፡ ስለነበሩ ፡ ሰዎች ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ይበዙ ፡ ዘንድ ፡ ስለዚህ ፡ ሚስት ፡ እንዲያገቡ ፡ ዕቁባት ፡ እንዲኖሩ ፡ ተፈቀደላቸው ። ምድር ፡ እንደመላች ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ዕቁባትን ፡ ከማኖር ፡ ከልክሎ ፡ ሚስት ፡ የማግባትን ፡ ሕግ ፡ ሠራ ።

## አንቀጽ ፳ወ፯ ።

በእንተ ፡ ሀብት ።

፪፻፸ ወመብዝኅቱኒ ፡ እመጽሐፈ ፡ ጠስ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ፲ወ፫ቱ ፡ በእንተ ፡ ሀብታት ፡ ወከዊን ፡ ሀብታት ፡ ውእቱ ፡ ይከውን ፡ እምኔሁ ፡ ገጻት ። ወውእቶሙ ፡ ሀብት ፡ ወወሀቢ ፡ ወዘይሁብዎ ፡ ሎቱ ፡ ወንዋይኒ ፡ ዘይሁቡ ፡ ኪያሁ ፡ ወተረፈ ፡ ትእዛዝ ።

፪፻፸፩ ሀብትሰ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ የሀብዎሙ ፡ ለእለ ፡ ኢኮኑ ፡ ድልዋነ ፡ ለመጽውቶ ፡ ወምጽዋትኒ ፡ ትከውን ፡ ለዘይደልዎ ። ወሀብትሰ ፡ ምግባረ ፡ ትሩፋት ፡ ይእቲ ፡ ዘይደሉ ፡ ውሂቦታ ፡ እምድኅረ ፡ ምጽዋት ። ወእምከመ ፡ ወሀበ ፡ ወሃቢ ፡ ኪያሃ ፡ ወተወክፈ ፡ ዘይሁብዎ ፡ ሎቱ ፡ ንዋየ ፡ ዘትትወሀብ ፡ ወእምዝ ፡ ይደሉ ፡ ሎቱ ፡ ሥልጣን ፡ ላዕሌሁ ፡ ወይሥራዕ ፡ ቦቱ ፡ ከመ ፡ ወሀቢሁ ።

፪፻፸፪ ወለወሀቢኒ ፡ ኢትከውን ፡ እማን ፡ እምኔሁ ፡ ሀብት ፡ ለእመ ፡ ኢኮነ ፡ ብጹሐ ፡ እምዐቅን ፡ ወማእምረ ፡ ወእግዚእ ፡ ወኅሩየ ፡ በአልቦቱ ፡ ፍርሃት ፡ እምዘወሀበ ። ወእመሰ ፡ ዘይፈርህ ፡ እምዘ ፡ ወሀበ ፡ ኢይትፈጸም ፡ ሎቱ ፡ ወእመኒ ፡ ሞተ ፡ ወሀቢሁ ፡ ኢይግባእ ፡ እምኔሃ ፡ በስምዐ ፡ ውኩፍ ፡ ኢበኀቡእ ፡ ወኢ ፡ በከሙት ።

፪፻፸፫ ወለወሀቢሰ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ የሀብ ፡ በሕይወቱ ፡ እመ ፡ ፈቀደ ፡ በጊዜሁ ፡ ዘእንበለ ፡ ውሳኔ ዕድሜ ። ወለእመ ፡ ፈቀደ ፡ እምድኅሬሁ ፡ በትእዛዝ ፡ ወበጊዜ ፡ እሙር ፡ ዘይመጽእ ፡ ወሎቱ ፡ ድልው ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ በጊዜ ፡ ሞቱ ፡ ተፍጻሜተ ፡ እምድኅረ ፡ ዕረፍቱ ።

## አንቀጽ ፡ ፳፯ ።

ስለ ፡ ስጦታ ፡ ይናገራል ።

፪፻፸ አብዛኛውም ፡ ከጠስ ፡ መጽሐፍ ፡ የተገኘ ፡ ነው ። ጠስ ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ። ስለስጦታዎች ፡ ይናገራል ። የስጦታ ፡ ሁኔታ ፡ ከ፫ ፡ ወገን ፡ ነው ። እነዚህም ፡ ስጦታ ፡ ሰጪ ፡ ለእርሱ ፡ የሚሰጡት ሰው ፡ እርሱን ፡ የሚሰጡት ፡ ገንዘብ ፡ ከትእዛዝ ፡ የቀረውም ፡ ናቸው ።

፪፻፸፩ ስጦታስ ፡ ምጽዋት ፡ ለመስጠት ፡ ለማይችሉት ፡ ሰዎች ፡ ሊሰጡአቸው ፡ ይገባል ። ምጽዋትም ፡ ለሚገባው ፡ ትሆናለች ። ስጦታስ ፡ ከምጽዋት ፡ ቀጥሎ ፡ ሊሰጡት ፡ የሚገባ ፡ የትሩፋት ፡ ሥራ ፡ ናት ። ሰጪ ፡ እርሷን ፡ ከሰጠ ፡ የምትሰጠዋንም ገንዘብ ፡ የሚሰጡት ፡ ሰው ፡ ከተቀበለ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንደሰጪው ፡ ይሠራበት ፡ ዘንድ ፡ በገንዘቡ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ሊኖረው ፡ ይገባል ።

፪፻፸፪ ሰጪውም ፡ እካለ ፡ መጠን ፡ ያደረሰ ፡ እዋቂ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ የተመረጠ ፡ ከሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ የተነሣ ፡ ፍርሀት ፡ የሌለበት ፡ ካልሆነ ፡ ስጦታው ፡ የታመነች ፡ አትሆንም ። ከሰጠ ፡ በኋላ ፡ የሚፈራ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ አይጸናለትም ። ሰጪው ፡ ቢሞትም ፡ በስውርም ፡ ቢሆን ፡ በግልጽ ፡ ስጦታው ፡ ተቀባይነት ፡ ባለው ፡ ምስክር ፡ ከተረጋገጠ ፡ አይመለስ ።

፪፻፸፫ ለሰጪ ፡ ግን ፡ በሕይወት ፡ ሳለ ፡ ዘመን ፡ ሳይወስን ፡ በጊዜው ፡ ሊሰጥ ፡ ቢወድ ፡ መስጠት ፡ ይገባዋል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በማዘዝና ፡ በሚመጣው በታወቀ ፡ ጊዜ ፡ ቢወድ ፡ ፍጻሜውን ፡ በሞቱ ፡ ጊዜ ፡ ሊያደርግ ፡ ይገባዋል ።

እንቀጽ ፡ ፵፯ ።

፱፻፷፩ ለእመ ፡ ወሀበ ፡ ነገሮ ፡ ንዋዮ ፡ እው ፡ መብዝ
ኀቶ ፡ በዘመን ፡ ኀበ ፡ ዘኢኮነ ፡ ሎቱ ፡ ወልድ ፡
ባቲ ፡ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ተወልደ ፡ ሎቱ ፡
ወልድ ፡ ሎቱኒ ፡ ይደልዎ ፡ እግብኦቱ ፡ ለዘረ
ቀደ ፡ ወለዘከመዝ ፡ ግብር ፡ ውስቴቱ ፡ ዘአሰተ
ተርአየ ፡ ሎቱ ፡ እመ ፡ ኮነ ፡ ወርቀ ፡ ዘወሀበ ፡
ለእመ ፡ ኮነ ፡ ርኩበ ፡ ወእመ ፡ አኮ ፡ ሤጦ ፡
ዚአሁ ።

፱፻፷፪ ወኢይክሉን ፡ አግብኦተ ፡ ንዋዩ ፡ እምድኅረ ፡
ሞተ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ወኢሰበ ፡ ተንሥአ ፡
ርእሰ ፡ ንዋዩ ፡ ዘወሀበ ፡ ሎቱ ፡ ወሤጠ ፡
ዚአሁ ። ወኢ ፡ ለእመ ፡ አኀዘ ፡ ወሃቢ ፡ ህየን
ቴሁ ፡ ለዘተውህበ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘተግምሮ
ቱሙ ፡ ወኢ ፡ በዘየመጽእ ፡ ሕሠም ፡ በጊዜ ፡
አግብኦቱ ፡ ለዘወሀቦ ፡ ንዋዩ ፡ ዚአሁ ፡ በከመ ፡
ለእመ ፡ ወሀበ ፡ ቤተ ፡ ወሐነጸ ፡ ውስቴቱ ፡
ሐውረ ፡ ኢይደልዎ ፡ ሎቱ ፡ አግብኦት ፡ ኪያሁ ፡
አላ ፡ ሤጦ ፡ ንዋዩ ።

፱፻፷፫ ወለእመ ፡ ወሀበ ፡ ሀብተ ፡ ዘኢበጽሐ ፡ መጠነ ፡
እከል ፡ ለመንሂ ፡ እምሰብእ ፡ ሎቱኒ ፡ ይደልዎ፡
ይትናገር ፡ በእንቲአሃ ፡ እምድኅረ ፡ በጽሐቱ ፡
ኀበ ፡ መጠነ ፡ እከል ፡ በ፳ቱ ፡ ዓመት ፡ ወይግ
ባእ ፡ ከመ ፡ ይንሣእ ፡ ንዋዮ ፡ ለእመ ፡ ፈቀደ ።

፱፻፷፬ መኑ ፡ ፲፱ ፡ ወሀብትስ ፡ እንተ ፡ ትትቀወም ፡
በመጽሐፍ ፡ ኢትትፈጸም ፡ ዘእንበለ ፡ የሀብ ፡
ወሃቢ ፡ መጽሐፈ ፡ ለዘይሁብ ፡ ሎቱ ፡ ለእመ ፡
ኮነት ፡ ለነኪር ፡ ኢይደልዎ ፡ ሎቱ ፡ እምድኅረ፡
ወሀበ ፡ ኪያሃ ፡ ከመ ፡ ይሚጥ ፡ እምኔሁ ።

፱፻፷፭ ወለእመኒ ፡ ኮነት ፡ ለወልድ ፡ ዘእሁ ፡ እው ፡
ለወልዱ ፡ ወልዱ ፡ ትከውን ፡ አማን ፡ ዘእንበለ ፡
መጽሐፍ ። ወይደሉ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይሚጥ ፡
በሕይወቱ ፡ ወከመ ፡ ይወልጥ ፡ በተጽሕፈ ፡
ሎሙ ፡ በከመ ፡ ፈቀደ ፡ ይደልዎ ።

፱፻፷፮ ወእምድኅረ ፡ ሞቱስ ፡ ሎሙ ፡ ዘውስተ ፡ መጽ
ሐፍ ፡ ወለእመኒ ፡ ኢወሀቦሙ ፡ ሎሙ ፡ ወእ
ለሂ ፡ ይሁቦሙ ፡ ቀዳሚ ፡ እሉ ፡ እሙንቱ ፡
ይቀድሙ ። ወድኅሬሆሙ ፡ ወላዲያኒሁ ፡ ወእምዝ ፡
አዝማዲሁ ፡ ወእምዝ ፡ ሐማን ፡ ወእምዝ ፡ ሐዋ
ኒሁ ፡ ወእምዝ ፡ ፍቁራን ፡ ወእምዝ ፡ ሳእከን ፡
ወእምዝ ፡ እግዋር ፡ ምእመናን ፡ ወእብያጽ ፡
ወዘይመስሎሙ ። ወይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡
ሰረና ፡ ለዘይደልዎ ፡ ሰረና ፡ በከመ ፡ ውሉድ ።

ስለ ፡ ስጦታ ። (ሀብት)

፱፻፷፩ ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ ወይም ፡ አብዛኛውን ፡ ገንዘ
ቡን ፡ ልጅ ፡ ባልወለደበት ፡ ዘመን ፡ ቢሰጥ ፡
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ልጅ ፡ ቢወለድለት ፡ ለወደደው ፡
ሊመልሰው ፡ ይገባዋል ። እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡
ሳገጠመው ፡ ሰው ፡ የሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ወርቅ ፡
ቢሆን ፡ ቢገኝ ፡ ገንዘቡን ፡ ባይገኝ ፡ ዋጋውን ፡
ይስጥ ።

፱፻፷፪ ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የሰጠው ፡
የገንዘቡ ፡ ዓይነትና ፡ ዋጋው ፡ ቢታጣ ፡ ገንዘቡ፡
መመለስ ፡ አይሆንም ። (አይጸናም) ። ሰጪ ፡
ስለተሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ፊንታ ፡ ሳይስማሙ ፡
ቢቀር ፡ የሰጠውን ፡ ገንዘብ ፡ በሚመልስበት ፡
ጊዜ ፡ ጉዳት ፡ በሚያመጣበት ፡ ገንዘብ ፡ ቤት ፡
ቢሰጥ ፡ በግቢው ፡ አጥር ፡ ቢያጥር ፡ ዋጋውን ፡
እንጂ ፡ እርሱን ፡ መመለስ ፡ እንደማይገባው ።

፱፻፷፫ እከለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ከሰው ፡ ወገን ፡ ለማ
ንም ፡ ስጦታ ፡ ቢሰጥ ፡ እከለ ፡ መጠን ፡ ከደ
ረሰ ፡ በኋላ ፡ በአራት ፡ ዓመት ፡ ስለእርሷ ፡ ሊና
ገር ፡ ይገባዋል ። ገንዘቡን ፡ ሊመልስ ፡ ቢወድ ፡
ይውሰድ ።

፱፻፷፬ መኑ ፡ ፲፱ ። በጽሑፍ ፡ የምትጸና ፡ ስጦታ ፡ ግን፡
ለባዕድ ፡ ከሆነች ፡ ሰጪ ፡ ለሚሰጠው ፡ በደብ
ዳቤ ፡ ካልሰጠው ፡ ስጦታው ፡ አይጸናም ። እር
ሷን ፡ ከሰጠው ፡ በኋላ ፡ ከእርሱ ፡ ሊመልሳት ፡
አይገባውም ።

፱፻፷፭ ለልጁ ፡ ወይም ፡ ለወንድ ፡ ልጁ ፡ ልጅ ፡ ቢሆን፡
ግን ፡ ያለ ፡ ጽሑፍ ፡ ይጸናል ። በሕይወት ፡ ሳለ፡
ሊመልሳት ፡ ለእርሱ ፡ ይገባል ። የተጻፈላቸው
ንም ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡ ሊለውጥ ፡ ይገባዋል ።

፱፻፷፮ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ በጽሑፍ ፡ ያለው ፡ የእነ
ርሱ ፡ ነው ። ባይሰጣቸውም ፡ የእነርሱ ፡ ነው ።
በመጀመሪያ ፡ የሚሰጣቸውም ፡ እሊህ ፡ ናቸው ።
ልጆች ፡ ከእነርሱም ፡ ቀጥሎ ፡ ወላጆቹ ፡ ከዚ
ያም ፡ በኋላ ፡ ዘመዶቹ ፡ ቀጥሎ ፡ አማች ፡ ቀጥሎ
አሳዳጊ ፡ ሞግዚት ፡ ቀጥሎ ፡ ወዳጆች ፡ ቀጥሎ ፡
አገልጋዮች ፡ ቀጥሎ ፡ የታመኑ ፡ ጐረቤቶች ፡
ጓደኞች ፡ የመሰሏቸውም ፡ ናቸው ። መተካከል ፡
ለሚገባው ፡ ማስተካከል ፡ ይገባል ። እነዚህም ፡
እንደ ፡ ልጆች ፡ ያሉ ፡ ናቸው ።

## አንቀጽ ፡ ፷፮ ።

፱፻፹ ወነሥኡ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘኢየአኀዙ ፡ ወሃቢሁ ፡ እላ ፡ የሐውር ፡ ኀበ ፡ እደዊ ፡ ገጽ ፡ እምገጸ ፡ ሕሠም ፡ ወእንዘ ፡ እዴሁ ፡ ላዕሌሁ ፡ በገመሃ ፡ ወእከዮ ፡ ወኮሕሉት ፡ ወእንትሉ ፡ ኀጕለ ፡ ሀቢየ ፡ እምእስተዋድዮቱ ፡ ለንዋእ ፡ ንዋዩ ፡ እው ፡ ገብረ ፡ በዘይማስን ፡ ሕይወቶ ፡ እው ፡ ኀደገ ፡ እምዘ ፡ ኮነ ፡ ተሰናእዎቶሙ ፡ ላዕሌሁ ፡ በትድሎሙ ፡ ሰማዕት ፡ በምንትኒ ፡ እምኵሉ ፡ ዘወሀቦ ፡ ሎቱ ፡ ወእምከመ ፡ ተዐውቀ ፡ ከሡተ ፡ በመንበረ ፡ ፍትሕ ፡ ወተጠየቀ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ገብረ ፡ እሐተ ፡ እምኒ ፡ እሉ ፡ ምግባራት ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ያግብእ ፡ ሀብታቲሁ ፡ ዘእንበለ ፡ ተውላጥ ፡ ለእመ ፡ ሀለዉ ፡ እው ፡ ሤጦ ፡ ዘእሆን ፡ ለእመ ፡ ኢሀለዉ ፡ ወለእመ ፡ ኢኀብሩ ፡ በምሳሌ ፡ ሤጥ ፡ ይኩን ፡ በከመ ፡ ቃሉ ፡ ለዘወሀቦ ፡ ሎቱ ፡ ለእመ ፡ ኢተንሥአ ፡ ቃለ ፡ ስምዕ ፡ ላዕሌሁ ፡ ዘያበጥል ፡ ቃሎ ።

፱፻፹፩ ወለእመኒ ፡ ይቤ ፡ ዘወሀብዎ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ጽኑስ ፡ ውእቱ ፡ እልቦ ፡ ዘይከልእ ፡ ነሢኦቶ ፡ ዘእንበለ ፡ በስምዕ ፡ ዘያዐርስ ፡ ነሢኦቶ ።

፱፻፹፪ ወኢይቀውም ፡ ሀብት ፡ ለዘይሁብዎ ፡ ዘእንበለ፡ ለዘቦቱ ፡ ጥሪት ፡ ወኢትትፌጸም ፡ ዘእንበለ ፡ ሶበ ፡ ይትዌከፉ ። ወንዋይሂ ፡ ዘይትወሀብ ፡ ኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ዘኢይትዐወቅ ፡ ወኢእምዘ ፡ ኢይከውኖ ፡ ለወሃቢ ፡ ምልክናሁ ።

፱፻፹፫ ወኢይኩን ፡ እንከ ፡ እምነ ፡ ዘተመውዐ ፡ ቦቱ ፡ ሕሊናሁ ፡ እስመ ፡ ዘይሁብዎ ፡ ኪያሁ ፡ ይበውእ ፡ ውስተ ፡ ልቡ ፡ ፍቅረ ፡ ንዋይ ፡ ወእመ ፡ እኮ ፡ ያደሉዎ ፡ በውእቱ ፡ ጊዜ ፡ ከመ ፡ ዘይሁብ ፡ ሰይፈ ፡ ለዘእኑዝ ፡ ጋኔን ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ቦ ፡ ዘይቀትል ፡ ቦቱ ፡ ነፍሶ ፡ እው ፡ ነፍሰ ፡ ካልኡ ።

፱፻፹፬ ወእመሰ ፡ ኮነ ፡ ንዋይ ፡ ዘተውህበ ፡ ኢይትፌለጥ ፡ ለተፈቅዶ ፡ ወኢበውሂብ ፡ ከመ ፡ ዘዲናራት ፡ ወጠፋልሐ ፡ ብሩር ፡ ኢይትፌቀድ ፡ ኀበ፡ ጽሒፍ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ እሙረ ፡ ለዝንቱሰ ፡ ይኩን ፡ ጽሕፈተ ፡ ዚአሁ ። ወበእንቲአሁ ፡ ይደሉ ፡ ጽሕፈተ ፡ ሰማዕት ፡ ዘያዜክሩ ፡ ባቲ ፡ ፍቅደ ፡ ንዋይ ፡ ዘይትወሀብ ፡ ወከዋኒ ፡ እርእያሁ ፡ ወያታ ፡ ትእዛዛቲሁ ፡ ለወሃቢ ፡ በእንቲአሁ ወከመ ፡ ውእቱ ፡ ኢይገብእ ፡ እምዘወሀበ ፡ ይደሉ ከመ ፡ ይጽሐፍ ፡ ትእዛዘ ፡ በእንቲአሁ ።

## ስለ ፡ ስጦታ ። (ሀብት)

፱፻፹ ከእነርሱም ፡ ወገን ፡ ሰጭውን ፡ የማያመሰግን ፡ ሁሉ ፡ ከክፋት ፡ ወገን ፡ ወደማናቸውም ፡ የክፋት ፡ ወገን ፡ የሚሄድ ፡ በበደል ፡ በክፋቱ ፡ በተንኮል ፡ እጁን ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ የእንጣ ፡ ገንዘቡን ለመውሰድ ፡ አንገር ፡ ሥራው ፡ የተነሣ ፡ ታላቅ ጥፋት ፡ ያጠፋው ፡ ወይም ፡ ሕይወቱ ፡ የሚጠፋበትን ፡ ሥራ ፡ ቢሠራ ፡ ወይም ፡ ከሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ በማናቸውም ፡ ነገር ፡ በምስክርች ፡ ፊት ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ የሆነውን ፡ ስምምነት የተወ ፡ (ያፈረሰ) ፡ በፍርድ ፡ አደባባይ ፡ በግልጽ ፡ ከታወቀ ፡ ከእነዚህም ፡ ሥራዎች ፡ አንዲቱን ፡ መሥራቱ ፡ ከተረጋገጠ ፡ ቢኖሩ ፡ ያለ ለውጥ ፡ ስጦታዎቹን ፡ ወይም ፡ ባይኖሩ ፡ ዋጋቸውን ፡ ይመልስለት ፡ ዘንድ ፡ ይገባዋል ። በዋጋው ፡ እምሳይ ፡ ባይስማሙ ፡ ቃሉን ፡ የሚያፈርስበት ፡ የምስክር ፡ ቃል ፡ ካልተነሣበት ፡ በቀር ፡ እንደሰጪው ፡ ቃል ፡ ይሁን ።

፱፻፹፩ የሰጡት ፡ ሰው ፡ ችጋረኛ ፡ እንደሆነ ፡ ቢናገርም ፡ ፍላጎቱን ፡ ከሚያስቀር ፡ ምስክር ፡ በቀር፡ ፍላጎቱን ፡ የሚከለክል ፡ የለም ።

፱፻፹፪ ስጦታ ፡ ለሚሰጡት ፡ ሰው ፡ ገንዘብ ፡ ላለው ፡ ሰው ፡ ካልሆነ ፡ አይጸናም ። በሚቀበላትም ፡ ጊዜ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አትፈጸምም ። የሚሰጠውም ፡ ገንዘብ ፡ ያልታወቀ ፡ ሊሆን ፡ አይገባም። ለሰጪ ፡ ከማያዝዝበትም ፡ ወገን ፡ ሊሆን ፡ አይገባም ።

፱፻፹፫ እንግዲህ ፡ ልቡናው ፡ ድል ፡ ከሚነሣበት ፡ ወገን ፡ አይሁን ፡ እርሱን ፡ የሚሰጡት ፡ ሰው ፡ በልቡ ፡ ፍቅረ ፡ ንዋይ ፡ ያድርበታልና ። ይህም፡ ባይሆን ፡ ወዲያው ፡ ያስምመዋል ። ጋኔን ፡ ለያዘው ፡ ሰው ፡ ሰይፍ ፡ እንደመስጠት ፡ ነው ። ነፍሱን ፡ ወይም ፡ የሌላውን ፡ ነፍስ ፡ እንደሚገድል ፡ ያለ ፡ ነውና ።

፱፻፹፬ የተሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ በቊጥር ፡ የማይለይ ፡ ወይም ፡ በመስጠት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ዲናርና ፡ እንደተመዘነ ፡ ብር ፡ ያለ ፡ ቢሆን ፡ ሊጻፍ ፡ አያስፈልግም ። የታወቀ ፡ ቢሆን ፡ ይህንስ ፡ ሊጽፉት ፡ ይገባል ። የሚሰጠውን ፡ የገንዘብ ፡ ቊጥር የመልኩን ፡ ሁኔታ ፡ ስለእርሱም ፡ የሰጪን ፡ የትእዛዝ ፡ ስልት ፡ እርሷን ፡ የሚያስረዱ ፡ ምስክሮችን ፡ ስለእርሱ ፡ መጻፍ ፡ ይገባል ። እርሱም ከሰጠ ፡ በኋላ ፡ እንዳይመለስ ፡ ስለእርሱ ፡ ትእዛዙን ፡ ይጽፍ ፡ ዘንድ ፡ ይገባዋል ።

አንቀጽ ፡ ፳፯ ።

፱፻፹፭ ወለእመ ፡ ኮነት ፡ ዘተውህበት ፡ ሀገር ፡ ይእቲ ፡ ወእከል ፡ ዘትትጋባእ ፡ እምኔሃ ፡ ይእቲ ፡ ትደሉ ፡ ለዘውሁብ ፡ ሎቱ ፡ እምእመ ፡ ተጽሕፈ ፡ ሎቱ ፡ መጽሐፍ ፡ ወተመጠወ ፡ ኪያሁ ፡ ለእመ ፡ ኢተ እዘዘ ፡ ላዕሌሁ ፡ ካልእ ፡ እምዘ ፡ ተጽሕፈ ። ወእመሰ ፡ ተእዘዘ ፡ እክል ፡ ዘሀለወት ፡ ኢትኩን ፡ ሎቱ ፡ እላ ፡ ይሰደድ ፡ እምፍጻሜ ፡ ሀብት ፡ ወእመ ፡ ተወክፈ ፡ ውእቱ ፡ ዘውሁብ ፡ ሎቱ ፡ ይከውን ፡ ግብር ፡ ከመዝ ። ወተረፈ ፡ ትእዛዛ ትሂ ፡ እስመ ፡ ኢይትኤዘዝ ፡ ዘይትዐደው ፡ ፍጻሜ ፡ ሀብት ።

፱፻፹፮ ወእመ ፡ ወሀበ ፡ ፩ዱ ፡ ለመኑሂ ፡ ምንተኒ ንዋየ ፡ ወሞተ ፡ እምቅድመ ፡ ብጽሐቱ ፡ ኀቤሁ ፡ ኢይደልዎሙ ፡ ለወራሲያኒሁ ፡ ከመ ፡ ይሰድዎ ።

፱፻፹፯ ወለእመኒ ፡ ወሀበ ፡ ዘሀሎ ፡ ታሕተ ፡ ሐዓኒት ፡ በትእዛዘ ፡ እቡሁ ፡ እው ፡ በትእዛዘ ፡ ርእሱ ፡ መጠነ ፡ ውእቱ ፡ ሀብት ፡ ይኩን ፡ ለአብ ። ወዘ ወሀበሂ ፡ ለብእሲ ፡ ንዋየ ፡ በፈቃዱ ፡ በዓለ ንዋይ ፡ ውእቱ ፡ ወሃቢሁ ።

ስለ ፡ ብድር ።

፱፻፹፭ የተሰጠችው ፡ ሀገር ፡ (መሬት) ፡ ብትሆን ፡ እህ ልም ፡ ከእርሷ ፡ የሚገኝባት ፡ ብትሆን ፡ ደብ ዳቤ ፡ ከተጻፈለትና ፡ እርሱን ፡ ከተቀበለበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ለተሰጠው ፡ ሰው ፡ ትገባለች ። ከተጻፈው ፡ ሌላ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ካልታዘዘ ፡ ያለችው ፡ እህል ፡ ብትታዘዝለት ፡ ግን ፡ (መሬቱ) ፡ ለእርሱ ፡ አትሁን ። ከፍጹም ፡ ስጦታ ፡ ይለይ ፡ እንጂ ። እርሱ ፡ የተሰጠውን ፡ ቢቀበል ፡ ግድ ፡ እንደዚህ ፡ ይሆናል ። ከትእዛ ዛት ፡ የቀረውም ፡ የስጦታን ፡ ፍጻሜ ፡ የሚተ ላለፍ ፡ አይታዘዝምና ።

፱፻፹፮ አንዱ ፡ ሰው ፡ ለማንም ፡ ማናቸውንም ፡ ገንዘብ፡ ቢሰጥ ፡ ወደ ፡ እርሱም ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ ቢሞት ፡ ወራሾቹ ፡ ሊወስዱት ፡ አይገባቸውም።

፱፻፹፯ በሞግዚት ፡ ስር ፡ ያለ ፡ በአባቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ በራሱ ፡ ትእዛዝ ፡ ገንዘብ ፡ ቢሰጥ ፡ ስጦታውን ፡ መመጠን ፡ ለአባት ፡ ይሁን ። በፈቃዱ ለሰው ፡ ገንዘብን ፡ የሰጠ ፡ ሰው ፡ ሰጪው ፡ ባለ ገንዘቡ ፡ ነው ።

## አንቀጽ ፡ ፳ወ፰ቱ ።

በእንተ ፡ ልቃሕ ፡ ወአኀዝ ፡ ወተሐብዮ ፡ ወምግ ብና ።

፱፻፹፰ ልቃሕሰ ፡ ሀብት ፡ ይእቲ ፡ እምእዝማዲሃ ፡ ለምጽዋት ፡ ዘእዘዘ ፡ ባቲ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወከ ልእ ፡ ከመ ፡ ኢይእበዮ ፡ ኪያሃ ፡ በቃሉ ፡ ዘው ስተ ፡ ወንጌል ፡ ዘይቤ ፡ ለቅሑ ፡ ወኢትምትሩ ፡ ተስፋሁ ፡ ለ፩ዱሂ ፡ ወብሂሎቱኒ ፡ ለዘፈቀደ ፡ ይትለቃሕ ፡ እምኔከ ፡ ኢትክልኦ ።

፱፻፹፱ ወእስተሐምሞሂ ፡ በእንተ ፡ ፈድየ ፡ ልቃሕ ፡ ድልው ፡ ውእቱ ፡ ወፈድዮቱኒ ፡ በጊዜ ፡ ዘይትከ ሀላ ፡ ሕግ ፡ ውእቱ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ዳዊት ነቢይ ፡ "ይትለቃሕ ፡ ኃጥእ ፡ ወኢይፈዲ ፡ ጻድቅሰ ፡ ይምሕር ፡ ወይሁብ" ። ወተዓግሦ ላለሰ ፡ ተለቃሒ ፡ እስከ ፡ ይረክብ ፡ ዘይፈድዮ ፡ ድልው ፡ ውእቱ ፡ ሎቱ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ኢትትኀሠሥ ፡ እምዘ ፡ ይነሥእ ፡ ንዋየከ ፡ ወኢታገብሮ ፡ በእንተ ፡ ግብረ ፡ ተጽ ናሱ ። ወእንበረ ፡ በእንቲአሁ ፡ ምሳሌ ፡ እግዚ እነ ፡ በገብር ፡ ዘአገበሮ ፡ ለበዓለ ፡ ዕዳሁ ።

## አንቀጽ ፡ ፳፰ ።

ስለ ፡ ብድር ፡ ስለ ፡ መያዣ ፡ ስለ ፡ ዋስትና ፡ ስለ ፡ አስተዳዳሪነት ፡ ይናገራል ።

፱፻፹፰ ብድርስ ፡ እግዚአብሔር ፡ እርሷን ፡ ከዘዘት ፡ ከምጽዋት ፡ ወገን ፡ የምትሆን ፡ ስጦታ ፡ ናት ። አበድሩ ፡ የአንዱንስ ፡ እንኳ ፡ ተስፋ ፡ አትቍረጡ ፡ ብሎ ፡ በወንጌል ፡ በተናገረው ፡ ቃሉ ፡ እርሷን ፡ እንቢ ፡ እንዳይል ፡ ከለከለ ። ከአንተ ፡ ሊበደር ፡ የሚሻውንም ፡ አትከልክለው ፡ በማ ለቱ ። (ማቴ ፡ ፭ ፡ ፵፪) ።

፱፻፹፱ ብድርንም ፡ ስለመክፈል ፡ መትጋት ፡ ተገቢ ፡ ነው ። በሚቻልበትም ፡ ጊዜ ፡ መክፈል ፡ ሕግ፡ ነው ። ኃጥእ ፡ ተበድሮ ፡ አይከፍልም ። ጻድቅ ፡ ግን ፡ ይራራል ፡ ይሰጣልም ፡ ብሎ ፡ ነቢይ ፡ ዳዊት ፡ እንደተናገረ ። (መዝ ፡ ፴፮ ፡ ፳፱) ፡ የሚከፍለውን ፡ እስ ኪያገኝ ፡ ድረስ ፡ በተበዳሪ ፡ ላይ ፡ መታገሥ ፡ ለአበ ዳሪ ፡ ይገባዋል ። ገንዘብህን ፡ ከወሰደ ፡ ሰው ፡ አትፈ ላልግ ፡ ስለችግሩም ፡ አታስገድደው ፡ ብሎ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ እንደተናገረ ። (ዘዳ ፡ ፲፭ ፡ ፫) ። ስለዚህም ፡ ጌ ታችን ፡ ባለዕዳውን ፡ ባስገደደው ፡ ባሪያ ፡ ምሳሌ ፡ ተናገረ ። (ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፳፫ - ፴፭) ።

## አንቀጽ ፡ ፳፮ ።

፱፻፺ ወሊቃሕሰ ፡ ያደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ በእንግዝ ፡ እው ፡ በትሕቢት ፡ እው ፡ በመድኅን ፡ እው ፡ በመጽሐፍ ፡ እንተ ፡ ውስቴታ ፡ ስማዕት ። ወናሁ ፡ ያብቍዕ ፡ በእንቲአሃ ፡ ጽሕፈተ ፡ እዴሁ ፡ ለዘተለቅሐ ፡ እው ፡ በዘይቀውም ፡ ላዕለ ፡ እሚኖቱ ፡ ባሕቲቱ ፡ ወስማዕታት ፡ ይልው ፡ በጽሕፈት ። ወይኩን ፡ ፍጡነ ፡ እው ፡ በስድሚ ፡ ወፈድዮ ፡ ልቃሕሰ ፡ ያደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ በጊዜሁ ፡ እመ ፡ ተኃሥሥ ፡ ወያደሉ ፡ ዓዲ ፡ ቅድመ ፡ ተኃሥሥ ፡ ጊዜ ፡ ተከሀሎ ።

፱፻፺፩ ወይኩን ፡ እምንዋየ ፡ ልቃሕ ፡ እው ፡ እምኀጡ ፡ በጊዜ ፡ ፈድዮ ፡ ዘተክሀሎ ፡ እምኔሆሙ ፡ እምተለቅሐት ፡ እው ፡ እምግብር ፡ ካልእ ፡ ኀጠ ፡ ዘሎሁ ፡ ጊዜ ፡ ፈድዮ ፡ መጠነ ፡ ልቃሕ ። ወለእመ ፡ ተገብረ ፡ በበይነ ፡ ዝንቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ይትገበር ፡ ከማሁ ። ወለእመ ፡ ይቤ ፡ ተለቃሒ ፡ ኀጣእኩ ፡ ከሃሊ ፡ በእንተ ፡ ፈድዮ ፡ ዕዳ ፡ ያደሉ ፡ ለለቃሒ ፡ ከመ ፡ ይኅሥእ ፡ እምዘ ፡ ረከበ ፡ እምንዋዩ ፡ በትእዛዘ ፡ ፈታሒ ፡ ወበዘመርዎ ፡ ውእተ ፡ ሰብእ ፡ ምእመናን ፡ በፍትሕ ፡ ወበሕሳብ ፡ ለእመ ፡ ኀረየ ፡ ዘንተ ፡ ተለቃሒ ፡ ወእመኒ ፡ ኢኀረየ ፡ ወለእመ ፡ ከሕደ ፡ ተለቃሒ ፡ ዘቦ ፡ ላዕሌሁ ፡ ዕዳ ፡ ወተከሥተ ፡ እምድኅረ ፡ ገብንቱ ፡ መጽሐፈ ፡ ስምዕ ፡ ዘሀሎ ፡ ኢያደሉ ፡ ይትኀወል ፡ ሎቱ ፡ ከይሃ ፡ አላ ፡ ይኅሥእ ፡ ኵሎ ፡ እምኔሁ ።

፱፻፺፪ ወዘሂ ፡ ከሕዶ ፡ ለበዓለ ፡ ዕዳሁ ፡ በዘዐለወ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወመሐለ ፡ ሎቱ ፡ ወእመ ፡ ቆሙ ፡ ስማዕታት ፡ ላዕሌሁ ፡ ያደልዎ ፡ ከመ ፡ ይፍዲ ፡ ሀየንተ ፡ ዝንቱ ፡ ምክሰቢተ ። ወእመሰ ፡ እምነ ፡ በጊዜ ፡ መሐላ ፡ እምድኅረ ፡ ከሕደ ፡ ድኅነ ፡ እምተኃሥሥተ ፡ ምክሰቢት ። ወዘክኅሂ ፡ በንግእ ፡ እንዘ ፡ ሰበ ፡ ኮነ ፡ እምዘ ፡ ቦቱ ፡ ዓስብ ፡ ወፃሬ ፡ ዘሉ ፡ ዘበጽሐ ፡ ኀበ ፡ እዴሁ ፡ ለለቃሒ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ያደሉ ፡ ይትኀወለሙ ፡ ላዕሌሁ ፡ በእምነት ፡ ዕዳሁ ።

፱፻፺፫ ወበእንተ ፡ ርዴስ ፡ ያደልወነ ፡ ከመ ፡ ንርኅቅ ፡ እምኔሁ ፡ እስመ ፡ ሕግ ፡ እምላኪዊ ፡ ናሁ ፡ ከልአ ፡ እምኔሁ ፡ ወለእመ ፡ ነሥአ ፡ ፅዱቀ ፡ ንዋየ ፡ በምንትኒ ፡ ግብር ፡ እምግብራት ፡ ወውእቱ ፡ ይከውን ፡ እምነ ፡ ሊቃሒ ፡ ወለእመ ፡ ተፈድየ ፡ እምበዓለ ፡ ዕዳሁ ፡ ያደልዎ ፡ እግብአቶ ፡ እንዘ ፡ ኀበ ፡ በዓለ ፡ ዚአሁ ። ወለእመ ፡

## ስለ ፡ ብድር ።

፱፻፺ ብድርስ ፡ በመያዣ ፡ ወይም ፡ በዋስትና ፡ ወይም ፡ በመድኅን ፡ ወይም ፡ ምስክሮች ፡ ባሉበት ፡ ጽሑፍ ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ። የተበዳሪ ፡ የእጅ ፡ ጽሕፈት ፡ እነዚህ ፡ ስለእርሱ ፡ ይጠቅማል ። ወይም ፡ በመተማመን ፡ ብቻ ፡ በማጸና ፡ ገንዘብ ፡ ነው ። ምስክሮችም ፡ ሊጻፉ ፡ ይገባል ። ፈጥኖ ፡ ወይም ፡ በቀጠሮ ፡ ይሁን ፡ ብድር ፡ መክፈልስ ፡ በተፈለገ ፡ ጊዜ ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ። ዳግመኛም ፡ በተቻለው ፡ ጊዜ ፡ ከፍላጎቱ ፡ አስቀድሞ ፡ መክፈል ፡ ይገባል ።

፱፻፺፩ ከብድር ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ከእነርሱ ፡ ወገን ፡ ከብድር ፡ የተቻለውን ፡ በመክፈል ፡ ጊዜ ፡ ከዋጋው ፡ ወይም ፡ በብድሩ ፡ ልክ ፡ በሚከፍልበት ፡ ጊዜ ፡ ከሌላው ፡ ሥራ ፡ ከዋጋው ፡ ይሁን ። ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ውል ፡ ቢደረግ ፡ እንደዚሁ ፡ ይሁን ። ተበዳሪ ፡ ብድርን ፡ ስለመክፈል ፡ ችሎታ ፡ እጣሁ ፡ ቢል ፡ በዳኛ ፡ ትእዛዝ ፡ ምእመናን ፡ ሰዎችም ፡ በፍርድና ፡ በግምት ፡ በመስኑ ፡ ገንዘብ ፡ ተበዳሪ ፡ ቢወድም ፡ ባይወድም ፡ ካገኘው ፡ ከገንዘቡ ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ ለአበዳሪ ፡ ይገባዋል ። ተበዳሪ ፡ ያለበትን ፡ ዕዳ ፡ ቢክድ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የያዘው ፡ የምስክር ፡ ደብዳቤ ፡ ቢመሰክርበት ፡ እርሷን ፡ ከቁጥር ፡ ሊያገቡለት ፡ አይገባም ። ሁሉን ፡ ከእርሱ ፡ ይውሰዱ ፡ እንጂ ።

፱፻፺፪ ስለ ፡ አለበት ፡ ዕዳ ፡ ባለዕዳውን ፡ የካደ ፡ ቢምልለትም ፡ ምስክሮች ፡ ቢመሰክሩበትም ፡ ስለዚህ ፡ ባጠፋው ፡ ሊከፍል ፡ ይገባዋል ። ከካደ ፡ በኋላ ፡ በመሐላ ፡ ጊዜ ፡ ቢያምን ፡ ግን ፡ እጠፋው ፡ ከመክፈል ፡ ዳነ ። መያዣ ፡ በመያዝ ፡ የሆነውም ፡ ዋጋና ፡ ፍሬ ፡ ካለው ፡ ወገን ፡ ቢሆን ፡ በአበዳሪ ፡ እጅ ፡ የደረሰው ፡ ሁሉ ፡ ስለዚህ ፡ በዕዳው ፡ ሊቆጠር ፡ ይገባል ።

፱፻፺፫ ስለ ፡ አራጣ ፡ ግን ፡ ከእርሱ ፡ ልንርቅ ፡ ይገባናል ። እምላካዊ ፡ ሕግ ፡ ከእርሱ ፡ ከልክሎ ልና ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ እንኳ ፡ ከሥራ ፡ በማናቸውም ፡ ሥራ ፡ ገንዘብ ፡ ቢቀበል ፡ እርሱ ፡ ከብድሩ ፡ ወገን ፡ ይሆናል ። ከባለ ፡ ዕዳው ፡ ቢቀበል ፡ መያዣውን ፡ ለባለቤቱ ፡ መመለስ ፡ ይገባዋል ። በብድሩ ፡ ላይ ፡ ቢጨምርም ፡ ጭማሪውን ፡

ወሰከ ፡ ላዕለ ፡ ሊቃሑ ፡ ይደልዎ ፡ አግብእተ ፡ ውሳኬ ፡ ወነቦሉ ፡ ዘአተፍአ ፡ እምንዋዩ ፡ ዓስቡ ፡ አው ፡ እምሤጠ ፡ ፍሬሁ ፡ ቦቱ ፡ ይትኃሠሥዎ ።

፱፻፶፬ ወይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይስተብ ፡ አንዘ ፡ በከመ ፡ የዐቅብ ፡ ንዋየ ፡ ዚአሁ ። ወለእመ ፡ ተኑየአ ፡ እምኔሁ ፡ ሰበ ፡ አተመ ፡ አኀዘ ፡ ሰማዕተ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ኢያተፍአ ፡ ኪያሁ ፡ ኢይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይፍዲ ። ወእመ ፡ አኮሰ ፡ ይደልዎ ፡ ለዘአኀዘ ፡ ከመ ፡ ያግብእ ፡ በጊዜሁ ፡ አው ፡ ቴመኑ ፡ ለዘተኃየአ ፡ እምኔሁ ። ወእመ ፡ ኮነ ፡ ዘተሰነአወ ፡ በሥርዓተ ፡ ውሳኔ ፡ ለእመ ፡ ጠፍአ ፡ እም ዘይደልዎ ፡ ለዘአኀዘ ፡ ቅድመ ፡ እኂዞቱ ፡ እም ጊዜ ፡ ተወፍዮቱ ፡ ፈቃሒ ፡ ይፍታሕ ፡ ላዕለ ፡ ሥርዓተ ፡ ውሳኔ ።

፱፻፶፭ ወሶበ ፡ ተኑየአ ፡ አንዘ ፡ ወእመ ፡ ኮነ ፡ ሚጠ ፡ ዚአሁ ፡ ዕሩየ ፡ ምስለ ፡ ሊቃሕ ፡ ተአተተ ፡ ተኃሥሦ ፡ እማእከሊሆሙ ። ወእመ ፡ ኮነ ፡ ዘይፈደ ፍዴ ፡ ይለዎ ፡ ለሊቃሒ ፡ ዘአኀዘ ፡ ከመ ፡ የሀብ ፡ ፍጻሜ ፡ ሚጡ ፡ ንዋየ ፡ ለአንዘ ። ወለእመሰ ፡ ኮነ ፡ ውሑዴ ፡ ይደልዎ ፡ ለተሊቃሒ ፡ ፈጽሞተ ፡ ሊቃሕ ፡ በጊዜ ፡ ዘይደሉ ፡ ወለዘተለቅሐሂ ፡ ይደ ልዎ ፡ ከመ ፡ ይትኀሠሥ ፡ ወያስተዋፅእ ፡ ላዕለ ፡ አንዘ ።

፱፻፶፮ ወሶበ ፡ ተሰነአወ ፡ ከመ ፡ ለእመ ፡ በጽሐ ፡ ዕድሜ ፡ ተፈድዮ ፡ ይሢጥዎ ፡ ለአንዘ ፡ ይነሥእ ፡ ዝንቱ ፡ ወኢይደልዎ ፡ ለአንዘ ፡ ከመ ፡ ይሢጦ ፡ ኪያሁ ፡ በሕጸጽ ፡ እምሤጠ ፡ ዚአሁ ፡ ወኢይ ወሌጥ ፡ እንበለ ፡ ትእዛዘ ፡ መኮንን ። ወእም ከመ ፡ ሚጠ ፡ በባሕቲቱ ፡ በዘየሐጽጽ ፡ እም ሚጡ ፡ ይትኃሠሥ ፡ ፍጻሜ ፡ ሤጥ ፡ ወይነሥእ ፡ ሐሳበ ፡ ሚጡ ፡ በከመ ፡ ቃሉ ፡ ለዘአኀዘ ፡ ምስለ፡ መሐላሁ ።

፱፻፶፯ ወእምሚጠ ፡ ሀለወ ፡ አንዘ ፡ ሀለወ ፡ ኀበ ፡ ሊቃሒ አው ፡ ኀበ ፡ ወራሲሁ ፡ ይለው ፡ አግብእቱ ፡ ለበ ዓለ ፡ ዚአሁ ፡ ሶበ ፡ ይፈዲ ፡ ዘተለቅሐ ፡ ዘእን በለ ፡ ዳእሙ ፡ ለእመ ፡ አቅደሙ ፡ ሥርዓተ ፡ ውሳኔ ፡ በዕድሜ ፡ እሙንቱ ። ወለእመ ፡ ኀለፈ ፡ ይደልዎ ፡ ለሊቃሒ ፡ ከመ ፡ ይምልክ ፡ ዘአኀዘ ፡ ሀየንተ ፡ ሤጡ ፡ ለሊቃሕ ፡ ዝንቱኒ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ሚጡ ፡ ዕሩየ ፡ ምስለ ፡ ሊቃሕ ።

፱፻፶፰ ወለእመ ፡ ሞተ ፡ ምንትኒ ፡ እምአንዘ ፡ አው ፡ አግንዞ ፡ አኃዚሁ ፡ አው ፡ መጽወየ ፡ አው ፡



መመለስ ፡ ይገባዋል ። ከዋጋው ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ከፍሬው ፡ ዋጋ ፡ ያጠፋውን ፡ ሁሉ ፡ ከእርሱ ፡ ይፈልጉ ። (ይጠብቁ) ።

፱፻፶፬ ገንዘቡን እንደሚጠብቅ ፡ አድርጎ ፡ መያዣውን ፡ ሊጠብቅ ፡ ይገባዋል ። ከእርሱም ፡ ቢጠፋ ፡ የያዘው ፡ ሰው ፡ እርሱ ፡ መያዣውን ፡ እንዳላ ጠፋ ፡ ምስክር ፡ ቢጠራ ፡ ሊከፍል ፡ አይገባውም ያም ፡ ባይሆን ፡ ግን ፡ ለያዘው ፡ ሰው ፡ በጊዜው፡ ሊመልስ ፡ ወይም ፡ ከእርሱ ፡ የጠፋውን ፡ መሰል ፡ ሊሰጥ ፡ ይገባዋል ። በውሳኔ ፡ ሥራት ፡ የተስማሙ ፡ ቢሆኑ ፡ ከመያዙ ፡ አስቀድሞ ፡ ከሚገባው ፡ ከያዘው ፡ ሰው ፡ ቢጠፋ ፡ ከተቀ በለበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ዳኛው ፡ በውሳኔው ፡ ሥራት ፡ ይፍረድ ።

፱፻፶፭ መያዣ ፡ በጠፋ ፡ ጊዜ ፡ ዋጋው ፡ ከብድሩ ፡ የተ ካከለ ፡ ቢሆን ፡ ከመካከላቸው ፡ ክርክር ፡ ተወ ገደ ። የሚበልጥ ፡ ቢሆን ፡ ሊያዘ ፡ አበዳሪ ፡ የመ ያዣውን ፡ ዋጋ ፡ ገንዘብ ፡ ፈጽሞ ፡ ሊሰጥ ፡ ይገ ባዋል ። ጥቂት ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ተበዳሪ ፡ በሚ ገባ ፡ ጊዜ ፡ ብድሩን ፡ መጨረስ ፡ ይገባዋል ። ለተበዳሪም ፡ መያዣውን ፡ ሊፈሳልግና ፡ ሊያወ ጣጣ ፡ ይገባዋል ።

፱፻፶፮ የሚከፈልበት ፡ ጊዜው ፡ ቢደርስ ፡ መያዣውን፡ ይሸጡት ፡ ዘንድ ፡ ቢስማሙ ፡ ይዘ ፡ ይሁን ። መያዣ ፡ ሊያዘ ፡ ሰው ፡ ከዋጋው ፡ በማጉደል ፡ እርሱን ፡ ሊሸጥ ፡ አይገባውም ። ያለዳኛም ፡ ትእዛዝ ፡ አይለውጥ ። ብቻውን ፡ ከዋጋው ፡ በሚያንስ ፡ ቢሸጠው ፡ የዋጋውን ፡ መጨረሻ ፡ ይፈልግ ። የዋጋውም ፡ ግምት ፡ ከመሐላ ፡ ጋራ፡ እንደ ፡ ያዠ ፡ ቃል ፡ ይሁን ።

፱፻፶፯ መያዣ ፡ በአበዳሪ ፡ ዘንድ ፡ ወይም ፡ በወራሹ ፡ ዘንድ ፡ የኖረውን ፡ ያህል ፡ ኑሮ ፡ ተበዳሪ ፡ በሚ ከፍልበት ፡ ጊዜ ፡ ለባለ ፡ ገንዘቡ ፡ መመለስ ፡ ተገባ ። በታወቀ ፡ ጊዜ ፡ የውሳኔውን ፡ ሥራት ፡ ቢያስቀድሙ ፡ ነው ፡ እንጂ ። ቢያልፍ ፡ ስለ ብድሩ ፡ ዋጋ ፡ የያዘውን ፡ እጅ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ለአበዳሪ ፡ ይገባዋል ። ይኸውም ፡ ዋጋው ፡ (መያዣው) ፡ ከብድሩ ፡ ጋር ፡ ስኩል ፡ ቢሆን ፡ ነው ።

፱፻፶፰ ከመያዣው ፡ ወገን ፡ ምንም ፡ ቢሞት ፡ ወይም ፡ ያዠ ፡ ነፃ ፡ ቢያወጣው ፡ ወይም ፡ ቢመጸው

አንቀጽ ፡ ፳፮ ።

ኰሎ ፡ ያለወ ፡ ከመ ፡ የሀብ ፡ ዘየንብቡ ፡ ሚጠ፡ ዚአሁ ፡ አው ፡ ፈድዮ ፡ ልቃሕ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ሰኑሰ ፡ ዘኢይትከሀሎ ፡ ፈድዮ ፡ ግዕዛን ፡ ወኢ ፡ ዘምጽዋት ፡ ወኢ ፡ ዘጕልት ፡ ዘእንበለ ፡ እምድኅረ ፡ ፈድዮ ፡ ልቃሕ ፡ ኢይደሉ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይሥራዕ ፡ ላዕለ ፡ አኀዘ ፡ በዘይበቍል ፡ በቀኖናተ ለቃሒ ፡ በጊዜሁ ፡ ዘከመ ፡ ሚጥ ፡ ወሀብት ፡ ወእመ ፡ አኮ ፡ በዘየሐፅፅ ፡ አኀዘ ፡ ከመ ፡ ንግድ ፡ ሐቡር ። ወይደሉ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይር ከብ ፡ በቀኖናተ ፡ ቦቱ ፡ በዘኢይረክቦ ፡ ሕሡም ፡ ለአኀዘ ፡ ዘከመ ፡ ፍሬያቲሁ ፡ ወተዋልዶቱ ፡ ወተዓስቦት ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ተዓስቦቱ ፡ ካልአ ፡ እምነ ፡ ሰድሚሁ ፡ ለልቃሕ ፡ ዘእንበለ ፡ እመ ፡ ተወሰነ ፡ ዝንቱ ።

፱፻ ፺፱ ወኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይረስዩ ፡ አኀዘ ፡ ዘኢይሜኒ፡ ሚጠ ፡ ዘከመ ፡ ኅብር ፡ ግዑዝ ፡ ወከመ ፡ ቤት ፡ ዘጕሉቱ ፡ ኪያሁ ፡ ለካልእ ፡ ወዘፍጡኑ ፡ ይማስን እምቅድመ ፡ ሰድሚሁ ፡ ለፈድዮ ፡ ልቃሕ ። ወእመ ፡ ተሣአሁ ፡ ከልኤሆሙ ፡ በእንተ ፡ ተወ ልጦተ ፡ አኀዝ ፡ ይኩን ፡ በከመ ፡ ቃሉ ፡ ለአ ኃዚ ፡ ምስለ ፡ መሐላሁ ። ወለእመ ፡ ይቤ ፡ ከመ፡ ውእቱ ፡ አግብአ ፡ ኀበ ፡ እግዚኡ ፡ ኢይትወ ከፉ ፡ ቃሎ ፡ ወእመኒ ፡ ፈድፈደ ፡ ንዋዩ ፡ አኀዝ፡ እምድኅረ ፡ አኀዘ ፡ ኢይፃእ ፡ እምእዴሁ ፡ ለዘ አኀዘ ። እመኒ ፡ ኮለንታሁ ፡ ወኢመንፈቁ ። ወለእመ ፡ ተሰነአዉ ፡ ከመ ፡ የሀሉ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ ዘአኀዘዎ ፡ አው ፡ ውስተ ፡ ፩ዱ ፡ ምእ መን ፡ ይደሉ ፡ ላዕሌሁ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ቦቱ ፡ በከመ ፡ ፈጸሙ ፡ ተሰናእዎ ፡ ላዕለ ፡ ዘተወሰነ። ወኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ ለቃሒ ፡ ወተለቃሒ ወዘተአመንዎሂ ፡ ሥልጣን ፡ ላዕለ ፡ አኀዝ ፡ ዘእ ንበለ ፡ ዘከመ ፡ ይደሉ ፡ ሥርዓቱ ። ወፍትሑ ፡ ወረሲሆ ፡ ለአኃዚ ፡ አኀዝ ፡ ወለዘሂ ፡ ተለቅሐ ፡ እምድኅረ ፡ ሞቶሙ ፡ ውእቱ ፡ ወከማሁ ፡ እለ ፡ ጸሐፉ ፡ ሎሙ ፡ በዘሐፈ ፡ ትእዛዝ ፡ በእንተ ፡ አኀዝ ፡ ወእለሂ ፡ አኰነንዎሙ ፡ በአኀዘ ፡ ሰዱ ፡ በውስተ ፡ ፍትሕ ። ወከማሁ ፡ ለእለ ፡ ሀለዉ ፡ ታሕተ ፡ ሕፅንነ ፡ በሕይወቶሙ ፡ ወእምድኅረ ፡ ሞቶሙ ። ወከማሁ ፡ ለፈታሒኒ ፡ እምድኅረ ፡ ተኀጥአቶሙ ፡ ለዝኩራን ።

፩ሺ. መከ ፡ ፃወጅቱ ፡ ወዘሎቱ ፡ ንዋይ ፡ ኀበ ፡

ስለ ፡ ብድር ።

ተው ፡ ወይም ፡ ቢጐልተው ፡ ስለእርሱ ፡ ፈንታ፡ ዋጋውን ፡ ሊሰጥ ፡ ወይም ፡ ብድሩን ፡ መክፈል ፡ ይገባዋል ። ነፃ ፡ የወጣውን ፡ የተመጸወተው ንም ፡ የተጐለተውንም ፡ ብድርን ፡ ከመክፈል ፡ በኋላ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ መክፈል ፡ የማይቻለው ድን ፡ ቢሆን ፡ በጊዜው ፡ ያበዳሪ ፡ ጥቅም ፡ ስለ ሚጠፋ ፡ በመያዣው ፡ ሊሠራበት ፡ አይገባ ውም ። ይኸውም ፡ እንደዋጋ ፡ እንደ ፡ ስጦታ ፡ ያለ ፡ ነው ። ያም ፡ ባይሆን ፡ መያዣ ፡ በሚጐ ድል ፡ ገንዘብ ፡ አጥርን ፡ እንደማፍረስ ፡ ነው ። መያዣውን ፡ ጉዳት ፡ በማያገኘው ፡ ገንዘብ ፡ በእርሱ ፡ ጥቅም ፡ ያገኝበት ፡ ዘንድ ፡ ይገባ ዋል ። ይኸውም ፡ እንደፍሬው ፡ እንደመ ዋለዱ ፡ እንደ ፡ ኪራዩ ፡ ነው ። ኪራዩ ፡ ከብድሩ፡ ጊዜ ፡ ሌላ ፡ ቢሆን ፡ ይዞ ፡ በተወሰነበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፱፻ ፺፱ ዋጋው ፡ ጥሩ ፡ ያይደለውን ፡ መያዣ ፡ ሊያደ ርጉ ፡ አይገባም ። ይኸውም ፡ ነፃ ፡ እንደወጣ ፡ ባሪያ ፡ እርሱን ፡ ለሌላ ፡ እንደጐለቱት ፡ ቤት ፡ ብድሩ ፡ ከሚከፈልበት ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ ፡ ፈጥኖ ፡ እንደሚጠፋ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ነው ። ስለመ ያዣው ፡ መለወጥ ፡ ሁለቱ ፡ ቢጣሉ ፡ ከመሐላ ው ፡ ጋር ፡ እንደያዥ ፡ ቃል ፡ ይሁን ። እርሱ ፡ ወደጌታው ፡ እንደመለስ ፡ ቢናገር ፡ ቃሉን ፡ አይ ቀበሉት ። ከያዘው ፡ በኋላ ፡ የመያዣው ፡ ገን ዘብ ፡ ቢበዛ ፡ መላውም ፡ ቢሆን ፡ እኩሌታውም ቢሆን ፡ ከያዥ ፡ እጅ ፡ አይውጣ ። ባስያዙት ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ወይም ፡ ከምእመናን ፡ በአንዱ ፡ እጅ ፡ እንዲኖር ፡ ቢስማሙ ፡ በተወሰነው ፡ ላይ ፡ ስምምነትን ፡ እንዳደረጉ ፡ ሊያደርግ ፡ ይገባል ። አበዳሪና ፡ ተበዳሪ ፡ አማኙም ፡ ሥራቱ ፡ እንደ ሚገባ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በመያዣው ፡ ሊሰለጥ ኑበት ፡ አይገባም ። ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ መያዣውን የያዘና ፡ የተበዳሪ ፡ የወራሽ ፡ ፍርድ ፡ ይህ ፡ ነው ። ስለመያዣ ፡ የትእዛዝ ፡ ደብዳቤ ፡ የጻ ፈላቸውና ፡ ሰዳውን ፡ በመያዝ ፡ የሾማቸው ፡ በፍርድ ፡ ጊዜ ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። በሕይወታቸ ውና ፡ ከሞታቸው ፡ በኋላ ፡ በሞግዚት ፡ ስር ፡ ላሉ ፡ እንዲሁ ፡ ነው ። እኒህ ፡ የተጠሩት ፡ (የተጠቀሱት) ፡ ከመታጣታቸው ፡ በኋላ ፡ ለዳ ኛውም ፡ እንዲህ ፡ ነው ።

፩ሺ. መከ ፡ ፃጅ ። ከሌላ ፡ ዘንድ ፡ ገንዘብ ፡ ያለው ፡

ካልእ ፡ ወኢ.ኅሡሦ ፡ እስከ ፡ ፴ ፡ ዓመት ፡ ኢ.ያ.
ያ.ልዎ ፡ እምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ተመይጠ ፡ ከመ ፡
ይኅሥሦ ፡ ኢ. ፡ ውእቱ ፡ ወኢ. ፡ ወልዱ. ፡ ወከ
ማሁ ፡ ይደሉ ፡ በግብረ ፡ ምግብኒ ። ወለእመ ፡
ሀሎ ፡ በእደ ፡ ሰብእ ፡ አኅዝ ፡ ወኢ.ወፅአ ፡ እም
እዴሁ ፡ ኀበ ፡ ትንየተ ፡ ካልኡ ፡ ሎቱ ፡ ይደሉ ፡
ከመ ፡ ይኅሥሥ ፡ ንዋዮ ፡ እሙ ፡ ከመ ፡ ይን
ሣእ ፡ አኀዘ ፡ ዘአኀዘ ፡ ወእመ ፡ ወፅአ ፡ አኀዝ ፡
እምእዴሁ ፡ ኀበ ፡ ካልኡ ፡ ኢ.ይደሉ ። ወከመዝ፡
ነገር ፡ ይደሉ ፡ ለኵሉ ፡ ተኀሥሦተ ፡ ሰዳ ፡ ወር
ስታት ፡ ወኵነኔያት ፡ ወሕገጋት ፡ ወተሳትፎ
ታት ፡ ወትዕግልታት ፡ ወውሳንያተ ፡ ምድር ፡
ወንዘትት ፡ ወሙሐዘ ፡ ማይ ፡ በውስተ ፡ ቤት ፡
ወሀገር ፡ ወገነታት ፡ ወዘይመስሎ ፡ ለዝንቱ ፡
ኢ.ይደልዎ ፡ ለ፩ዱ ፡ ከመ ፡ ይትኀሠሦ ፡ እም
ድኅረ ፡ ፴ ፡ ዓመት ፡ ወእመኒ ፡ ፈቀደ ፡ ተኀ
ሥሦ ፡ ኢ.ይፍትሑ ፡ ሎቱ ፡ በዝንቱ ።

፩ሺ.፩ መክ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ወእብኒ ፡ ኢ.ይትአኀዝ ፡ በሰዳ ፡
ሊቃሐ ፡ ወልዱ ፡ ለእመ ፡ ኢ.ኮነ ፡ ዘተለቅሐ ፡
በትእዛዘ ፡ ዚ.አሁ ። ወኢ.ይትአኀዝ ፡ ብእሲ ፡
በሊቃሐ ፡ ንዋየ ፡ እሙ ፡ ወእኁ ፡ በእኁሁ ፡
ወኢ. ፡ በአበ ፡ ብእሲቱ ፡ ዳእሙ ፡ እመ ፡ ተሐበ
ዮሙ ፡ ይፈዲ ።

፩ሺ.፪ ወበእንተ ፡ ሕቢ.ትሰ ወእድኅና ፡ ለሙ ፡ ፪ቱ ፡
ፍናዋት ፡ እድኅናሰ ፡ ዘነፍስ ፡ ውእቱ ፡ ወተሐ
ብዮ ፡ ዘንዋይ ። ወተሐብዮሰ ፡ ዘንዋይ ፡ ለዘተጠ
የቀ ፡ ንዋዩ ፡ ወሥርዓቱ ፡ ለዘከመዝ ፡ ይትጋኒ ፡
ትሕቢቱ ። ወእመ ፡ ኮነ ፡ ዘተሐበዮ ፡ ሎቱ ፡
ማእምረ ፡ አው ፡ ዐብደ ፡ ይደሉ ፡ እንከ ፡ ተሐ
ብዮ ፡ በትእዛዘ ፡ ዚ.አሁ ፡ ለዘተሐበይዎ ፡ ወለእ
መኒ ፡ ኮነ ፡ ዘእንበለ ፡ ትእዛዙ ። ወለእመ ፡ ተሐ
በዮ ፡ በትእዛዙ ፡ ይደሉ ፡ ተኀሥሦ ፡ እምኔሁ ፡
በኵሉ ፡ ዘፈደየ ፡ በእንቲአሁ ፡ ወለእመሰ ፡ ተሐ
በዮ ፡ ዘእንበለ ፡ ትእዛዙ ፡ ኢ.ይደሉ ፡ ተኀሥሦ ፡
እምኔሁ ፡ ዘእንበለ ፡ በዘፈደየ ፡ በእንቲአሁ ።

፩ሺ.፫ ወነገረ ፡ ተሐብዮሰ ፡ ከመዝ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡
ይበል ፡ ተሐበይኩከ ፡ አነ ፡ እገሌ ፡ ለእገሌ ፡
በዘከመዝ ፡ ወዘከመዝ ። ወለእመ ፡ ይቤ ፡ ተሐ
በይኩከ ፡ ለእገሌ ፡ በእንተ ፡ እገሌ ፡ ወለእመ ፡
ቆመ ፡ ላዕሌሁ ፡ ስምዕ ፡ ይደሉ ፡ ቦቱ ፡ በው
እቱ ፡ ጊዜ ፡ ዘኮነ ፡ ተሐብዩ ፡ ወእኮ ፡ በዘእምነ ፡
ቦቱ ፡ ዘተሐበዮ ፡ ዘእንበለ ፡ ሰማዕት ። ወለ
እመ ፡ ይቤ ፡ ዘተሐበየ ፡ ተሐበይኩ ፡ ውግረ ፡

ሰው ፡ እስከ ፡ ፴ ፡ ዓመት ፡ ባይፈልገው ፡ ከዚህ ፡
በኋላ ፡ እርሱም ፡ ቢሆን ፡ ልጁም ፡ ቢሆን ፡ ተመ
ልሶ ፡ ሊጠይቅ ፡ አይገባውም ። በአስተዳዳረን
ትም ፡ ሥራ ፡ እንደዚሁ ፡ ይገባል ። በከሳሽ ፡ እጅ፡
መያዣ ፡ ቢኖር ፡ ከእጁ ፡ ወደሌላው ፡ እጅንት ፡
ባይወጣ ፡ ለእርሱ ፡ ገንዘቡን ፡ ሊጠይቅ ፡ ወይም
የያዘውን ፡ መያዣ ፡ ሊይዝ ፡ ይገባዋል ። መያ
ዣው ፡ ከእጁ ፡ ወደሌላው ፡ ቢወጣ ፡ ሊጠይቅ ፡
አይገባም ። ሰዳን ፡ ለመፈላለግ ፡ ሁሉ ፡ እንደ
ዚህ ፡ ነገር ፡ ይገባል ። የርስትና ፡ የዳኝነት ፡
የሕግና ፡ የአንድነት ፡ ንግድ ፡ የቅሚያ ፡ የም
ድር ፡ ድንበር ፡ የጕድጓድ ፡ በቤትና ፡ በሀገር ፡
በተክልም ፡ በታ ፡ ያለ ፡ የውሀ ፡ በይ ፡ ይህን ፡
የመስለውም ፡ ለአንድ ፡ ሰው ፡ ከ፴ ፡ ዓመት ፡
በኋላ ፡ ሊጠይቅ ፡ አይገባውም ። ሊከራከር ፡
ቢወድም ፡ በዚህ ፡ አይፍረዱለት ።

፩ሺ.፩ መክ ፡ ፲፪ ። አባት ፡ በልጁ ፡ ብድር ፡ ሰዳ ፡ አይ
ያዝ ። በእርሱ ፡ ትእዛዝ ፡ የተበደረ ፡ ካልሆነ ፡
በቀር ። ሰው ፡ በእናቱ ፡ ገንዘብ ፡ ብድር ፡ አይ
ያዝ ፡ ወንድም ፡ በወንድሙ ፡ በሚስቱም ፡
አባት ፡ አይያዝ ። ነገር ፡ ግን ፡ ቢዋሳቸው ፡ ይከ
ፈል ።

፩ሺ.፪ ስለዋስትናና ፡ ስለመድን ፡ ግን ፡ ሁለት ፡
መንገዶች ፡ አሏቸው ። መድን ፡ የነፍስ ፡ ነው ።
ዋስትናም ፡ የገንዘብ ፡ ነው ። የገንዘብ ፡ ዋስ
ትና ፡ ግን ፡ ገንዘቡና ፡ ውሳኔው ፡ ለተረጋገጠ ፡
ለእንደዚህ ፡ ላለው ፡ ዋስትናው ፡ ያምራል ።
ለእርሱ ፡ የተዋሰው ፡ ሰው ፡ አዋቂ ፡ ወይም ፡
አላዋቂ ፡ ቢሆን ፡ በሚዋሱት ፡ ሰው ፡ ትእዛዝ ፡
ያለ ፡ ትእዛዙም ፡ ቢሆን ፡ እንግዲህ ፡ መዋስ ፡
ይገባል ። በትእዛዙ ፡ ቢዋሰው ፡ ስለእርሱ ፡ በከ
ፈለው ፡ ሁሉ ፡ ከእርሱ ፡ መጠየቅ ፡ ይገባል ።
ያለትእዛዙ ፡ ቢዋሰው ፡ ግን ፡ ከከፈለው ፡ በቀር ፡
ከእርሱ ፡ ሰዳ ፡ መፈለግ ፡ አይገባም ።

፩ሺ.፫ የመዋስም ፡ ነገር ፡ እንዲህ ፡ ነው ። እኔ ፡ እገሌ ፡
ለእገሌ ፡ እንደዚህና ፡ እንደዚህ ፡ ባለ ፡ ነገር ፡
ተውሼዋለሁ ፡ ይል ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ስለ ፡ እገሌ ፡
ለእገሌ ፡ ተውሼዋለሁ ፡ ቢል ፡ ምስክርም ፡ ቢመ
ሰክርበት ፡ ዋስ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡
መክፈል ፡ ይገባዋል ። ያለምስክር ፡ ዋሱ ፡ ባመ
ነበት ፡ አይደለም ። የተዋሰው ፡ ሰው ፡ ተውሼ
ዋለሁና ፡ ገንዘብህን ፡ ከባሕር ፡ ወይም ፡ ልብ

ንዋየከ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡ እው ፡ እልባሲከ ፡ ውስተ ፡ እሳት ፡ ኢይኅጉ ፡ ተሐብዮቱ ፡ ለዘኮነ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ እርእይ ።

፩ሺ.፬ ወዘይደልዎሂ ፡ ለሊቃሒ ፡ ከመ ፡ ይትኃሠሦ ፡ ቅድመ ፡ ለተለቃሒ ፡ ወለእመ ፡ ኢረደየ ፡ ይሕሩ ፡ ወይትኃሠሦ ፡ ለዘተሐበየ ። ወለእመ ፡ ርኅቀ ፡ ተለቃሒ ፡ የሀቦ ፡ ፈታሒ ፡ ለተሐባዪ ፡ ሰደሜ ፡ ወለእመ ፡ ኢረከቦ ፡ በውእቱ ፡ ሰደሜ ፡ እሜሃ ፡ ይስፋሕ ፡ እደዊሁ ፡ ለነሢእ ፡ ንዋዩ ፡ ለዘተሐበየ ፡ ተለቃሒ ፡ በእምባነ ፡ ሊቃሕ ፡ ለእመ ፡ ፈደየ ። ወእመ ፡ አኮሰ ፡ ይስፋሕ ፡ እደዊሁ ፡ ለቃሒ ፡ ኀበ ፡ ጥሪቱ ፡ ለተሐባዪ ፡ በእምባነ ፡ ሊቃሕ ።

፩ሺ.፭ ወይደልዎ ፡ ለሊቃሒ ፡ ተኃሥሦቶሙ ፡ ለተለቃሒ ፡ ወተሐባዪ ። ወለተሐባዪኒ ፡ ለእመ ፡ ተሐበዮ ፡ ካልዕ ፡ ይደልዎ ፡ ሎቱ ፡ ተኃሥሦተ ፡ ኵሎሙ ፡ ወለእመ ፡ ሞተ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ይደሉ ፡ ቦቱ ፡ ከመ ፡ ይትኃሠሦሙ ፡ እለ ፡ ተርፉ ፡ ወለእመ ፡ መሐሩ ፡ በኵሉ ፡ እምኔሆሙ ፡ ወእስተዳኃረ ፡ ኅሠሣሁ ፡ ይድኅን ፡ ተሐባዪ ፡ ወትድኅር ፡ ኅሠሣሁ ፡ ወኢይትኃሠሦ ። ወእመ ፡ ቦ ፡ ዘተረደየ ፡ እምኔሁ ፡ ውእቱ ፡ ሊቃሕ ፡ ተፀርዐ ፡ ተኃሥሦቶሙ ፡ በእንቲአሁ ፡ ለእለ ፡ ተርፉ ።

፩ሺ.፮ ወለእመ ፡ ኮኑ ፡ እለ ፡ ተሐበዩ ፡ ብዙኃነ ፡ ወለለ፩ዱ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ያስተቃልሉ ፡ ተዋሕሶቶ ፡ ይደልዎ ፡ ለዘነሥአ ፡ ሕቢቶሙ ፡ ከመ ፡ ይትኃሠሥ ፡ እምነ ፡ ኵሎሙ ፡ ኵሎ ፡ ንዋዮ ። ወዘሂ ፡ ነሥአ ፡ እም፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ይደልዎ ፡ ለገብኡ ፡ ፩ዱ ፡ ከመ ፡ ይትኃሠሦሙ ፡ ለለ፩ዱ ፡ እምእለ ፡ ተርፉ ፡ ዘወሀበ ፡ ለሊሁ ፡ ፈድፋደ ፡ እምነ ፡ ዘይደሉ ፡ ላዕሌሁ ፡ መንፈቆ ፡ ወራብዕተ ፡ እደ ፡ በእምሳለ ፡ ለእመ ፡ ኮኑ ፡ ፬ተ ፡ ወኢኮነ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘያስተቃልል ፡ እላ ፡ ኵሎሙ ፡ ኅቡረ ፡ ኢይደልዎሙ ፡ ለተሓባይያን ፡ ከመ ፡ ይትኃሠሥ ፡ ኵሎ ፡ ለለ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘእንበለ ፡ በዘይደልዎ ፡ ውሂበ ፡ ራብዕተ ፡ እደ ፡ ለእመ ፡ ኮኑ ፡ ፬ተ ።

፩ሺ.፯ ወለእመ ፡ ገብረ ፡ ሰርቀ ፡ ነግሴ ፡ ዋሕስ ፡ ምስለ ፡ በዓለ ፡ ንዋይ ፡ ዘተሐበዮ ፡ ሎቱ ፡ በእንተ ፡ ፩ዱ ፡ እምንዋይ ፡ ድኅነ ፡ ተሐባዪ ፡ ወዘተሐበዮሙ ፡ ሎሙ ፡ እምተኃሥሦተ ፡ በዓለ ፡ ዕዳ ፡ ወይከውን ፡ ተሐባዪ ፡ ተኃሥሦ ፡ ለዘተሠ



ስሆን ፡ ከእሳት ፡ ጣል ፡ ቢል ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ የሆነው ፡ ስው ፡ ዋስትና ፡ መልካም ፡ አይደ ለም ።

፩ሺ.፬ ላበዳሪም ፡ የሚገባው ፡ አስቀድሞ ፡ ተበዳሪን ፡ መጠየቅ ፡ ነው ። ባይከፍል ፡ ሄዶ ፡ ዋሱን ፡ ይጠ ይቀው ። ተበዳሪ ፡ ቢርቅ ፡ ዳኛ ፡ ለዋሱ ፡ ቀን ፡ (ቀጠሮ) ፡ ይስጠው ። በዚያ ፡ ቀጠሮ ፡ ባያገኘው ከከፈለ ፡ ዋስ ፡ የሆነውን ፡ የተበዳሪ ፡ ገንዘብ ፡ በብድሩ ፡ ልክ ፡ ለመውሰድ ፡ ያንጊዜ ፡ እጁን ፡ ይዘርጋ ። ይህም ፡ ባይሆን ፡ ግን ፡ እበዳሪ ፡ በብ ድሩ ፡ ልክ ፡ ወደዋሱ ፡ ገንዘብ ፡ እጁን ፡ ይዘ ርጋ ።

፩ሺ.፭ ለአበዳሪ ፡ ዋሱንም ፡ ተበዳሪውንም ፡ መያዝ ፡ ይገባዋል ። ሌላ ፡ ቢዋሰው ፡ (የጠለፉ ፡ ዋስ ፡ ቢኖረው) ፡ ሁሉቹንም ፡ መያዝ ፡ ይገባዋል ። ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ ቢሞት ፡ የቀሩት ፡ በዕዳው ፡ ሊጠየቁት ፡ ይገባል ። ከእነርሱ ፡ በሁሉ ፡ ቢም ረው ፡ መፈለጉንም ፡ ቢያቆይ ፡ ዋሱ ፡ ይዳን ። መያዙም ፡ ትቆይ ። እይፈላለጉት ። ከእርሱ ፡ ያን ፡ ብድር ፡ የተከፈለ ፡ ስው ፡ ቢኖር ፡ ስለእ ርሱ ፡ የቀሩት ፡ ስዎች ፡ ክርክር ፡ ተቋረጠ ።

፩ሺ.፮ ዋሶች ፡ ብዙዎች ፡ ቢሆኑ ፡ ለእያንዳንዳቸው ፡ ዋስነታቸውን ፡ ያስወርዱ ። ዋስነታቸውን ፡ ለተቀበለ ፡ ስው ፡ ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ ከሁላቸው ፡ ሊቀበል ፡ ይገባዋል ። ከእነርሱ ፡ ወገን ፡ ከአ ንዱ ፡ የወሰደም ፡ ለእርሱ ፡ ከሚገባው ፡ እብ ልጦ ፡ እርሱ ፡ የሰጠውን ፡ እኩሌታውንና ፡ አራት ፡ እጁን ፡ ከቀሩት ፡ ስዎች ፡ እያንዳንዱን ፡ ሊጠይቃቸው ፡ ለዚያ ፡ ለአንዱ ፡ ስው ፡ ይገባ ዋል ። ለምሳሌ ፡ አራት ፡ ቢሆኑ ፡ ሁሉም ፡ በአ ንድነት ፡ እንጂ ፡ ከእነርሱ ፡ ፩ዱ ፡ የሚከፍል ፡ አይደለም ። አራት ፡ ቢሆኑ ፡ ከእነርሱ ፡ እያንዳን ዱ ፡ አራተኛውን ፡ እጅ ፡ መስጠት ፡ በሚገባው፡ ገንዘብ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሁሉን ፡ ይከፍሉ ፡ ዘንድ ፡ ለዋሶች ፡ አይገባቸውም ።

፩ሺ.፯ ዋስ ፡ የጠራ ፡ ከገንዘብ ፡ ወገን ፡ ስለአንዱ ፡ ከተ ዋሰው ፡ ባለገንዘብ ፡ ጋራ ፡ ዕርቅ ፡ ቢያደርግ ፡ ዋሱ ፡ ዳነ ። ለእነርሱም ፡ የተዋሳቸው ፡ ከበዓለ ዕዳው ፡ መፈላለግ ፡ ዳነ ። ዋሱ ፡ በታረቀበት ፡ ልክ ፡ ለተዋሰው ፡ ስው ፡ ተያዥ ፡ ይሆናል ።

ሕስ ፡ ሎቱ ፡ በአምጣነ ፡ ዘተዓረቀ ፡ ቦቱ ።

፩ሺ.፹፰ ወይደሉ ፡ ለሥርዓተ ፡ ሕቢት ፡ በገቢረ ፡ ውሳኔ ፡ ወይበል ፡ ተሐባዪ ፡ እን ፡ ተሐበይክዎ ፡ ለእ ገሊ ፡ ከመገ ፡ እስከ ፡ ኅበዝ ። ወማእዜኒ ፡ ይደ ልዎ ፡ ለተሐባዪ ፡ በንዋይ ፡ ከመ ፡ የሀብ ፡ ለዘተ ሐበዮ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይድኅን ፡ እምዕዳ ።

፩ሺ.፹፱ ወእመሰ ፡ ተሰነአወ ፡ ተሐባዪ ፡ ወንግሊ ፡ ዋሕስ ፡ ላዕለ ፡ ንዋይ ፡ ይደልዎ ፡ ይፍዲ ፡ ተሐ ባዪ ፡ ንዋየ ፡ ንግሊ ፡ ዋሕስ ፡ ወይደልዎ ፡ ቀዊም ፡ ላዕለ ፡ ንዋይ ፡ እስከ ፡ ይትኅሠሥ ፡ ንግሊ ፡ እምኔሁ ። ወለእመ ፡ ረብኑ ፡ ቦቱ፡ ተሐባዪ ፡ በዘንሥአ ፡ እው ፡ ኀጕለ ፡ ዝንቱ ፡ ይደሉ ፡ ሎቱ ። ወኢይደልዎ ፡ ለመኑሂ ፡ በዓለ ፡ ዕዳ ፡ ከመ ፡ ይትከላእ ፡ እምተመጥዎቱ ፡ ዘወ ሀቦ ፡ ሎቱ ፡ ተለቃሒ ፡ በጊዜ ፡ ወሀበ ፡ ወበ ከሮሉ ፡ ንዋይ ፡ ኢይደሉ ፡ ተረድኦቱ ፡ እምተሐ ባዪ ፡ ለእመ ፡ ኢኮነ ፡ አማን ፡ ተሐብዮቱ ፡ በከመ ፡ ፍትሐ ፡ ሕግ ።

፩ሺ.፺ ወለእመ ፡ ሞተ ፡ ዘተሐበይዎ ፡ ይደልዎ ፡ ለተ ሐባዪ ፡ ተኀሥሦ ፡ እምወራስያኒሁ ፡ በዘተሐ በየ ፡ ኪያሁ ፡ ለእመ ፡ ቦቱ ፡ ጥሪት ። ወለእመኒ ፡ ሞተ ፡ ተሐባዪ ፡ ይደልዎ ፡ ተኀሥሦ ፡ ለንግሊ ፡ ዋሕስ ፡ እምእደ ፡ ወራስያኒሁ ፡ እመ ፡ ቦነ ፡ ሎቱ ፡ ንዋይ ። ወለእመ ፡ አልቦቱ ፡ ንዋይ ፡ ኢይትኀሠሥ ፡ እምዘ ፡ ኢኮነ ፡ ሎቱ ፡ ዋሕስ ።

፩ሺ.፺፩ ወመድኅነ ፡ ነፍስኒ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ያምጽእ ፡ ዘተድኅነ ፡ ወይኩን ፡ ቃለ ፡ ዘቲ ፡ ተድኅኖ ፡ ከመ ፡ ይበል ፡ ተድኅንኩ ፡ ለአብጽሖተ ፡ እገሌ፡ ለእገሊ ፡ እው ፡ ተድኅንኩ ፡ ለእገሊ ፡ ገጸ ፡ እገሊ ፡ እው ፡ ላዕሌየ ፡ ተድኅኖተ ፡ እገሊ ። ወለእመ ፡ ሠርዐ ፡ ዕድሜ ፡ እሙረ ፡ በእይኒ ፡ ጊዜ ፡ ይትኀሠሥዎ ፡ ኅሡሣ ፡ ለዘተድኅነ ፡ አመ በጽሐ ፡ ዕድሜ ፡ ወበጊዜ ፡ የኀሥሥ ፡ እም ኔሁ ፡ ዘኮነ ፡ ሎቱ ፡ መድኅነ ። ወለእመ ፡ አብ ጽሖ ፡ እምቅድመ ፡ ውእቱ ፡ ጊዜ ፡ አመ ፡ ይት ከሀሎ ፡ እኁዞቱ ፡ ለበዓለ ፡ ዕዳሁ ፡ ድኅነ ፡ እምኔሁ ፡ ወከማሁ ፡ ለእመ ፡ እግብአ ፡ ነፍሶ ፡ ለበዓለ ፡ ዕዳሁ ። ወእመኒ ፡ ኢተረክበ ፡ እምድ ኅረ ፡ ዕድሜ ፡ ዘተሠርዐ ፡ የሀቦ ፡ ፈታሒ ፡ ዕድሜ ፡ መዋዕለ ፡ እስከ ፡ ያመጽእ ። ወለ እመ ፡ ኢያምጽእ ፡ እምድኅረ ፡ ዕድሜሁ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘተሐበየ ፡ ሎቱ ፡ ገጸ ፡ ባሕቲቱ ፡ ተእኀዘ ፡ በአብጽሖተ ፡ ባሕቲቱ ። ወእመኒ ፡



፩ሺ.፹፰ የዋስነት ፡ ሥራት ፡ ውሳኔ ፡ እንዲኖረው ፡ ይገ ባል ። ዋሱ ፡ እኔ ፡ ለእገሌ ፡ ከዚህ ፡ እስከ ፡ ዚህ ፡ ተውሼዋለሁ ፡ ይበል ። መቼውንም ፡ ከዕዳው ፡ ይድን ፡ ዘንድ ፡ ለተዋሰው ፡ ሰው ፡ ሊሰጥ ፡ በገ ንዘብ ፡ ዋስ ፡ ለሆነ ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ.፹፱ ዋሱና ፡ ዋስ ፡ የጠራው ፡ በገንዘቡ ፡ ቢስማሙ ፡ ዋስ ፡ የጠራ ፡ ገንዘቡን ፡ ሊከፍል ፡ ይገባዋል ። ተቀባዩ ፡ ከእርሱ ፡ እስኪፈልገው ፡ ድረስ ፡ በገንዘቡ ፡ ማዘዝ ይገባዋል ። ዋሱ ፡ በተቀበለ ው ፡ ገንዘብ ፡ ቢጠቀምበት ፡ ወይም ፡ ቢጠፋ በት ፡ ይህ ፡ ለእርሱ ፡ ይገባል ። ለማንም ፡ ባለዕዳ ፡ ተበዳሪ ፡ በሰጠው ፡ ጊዜ ፡ የሰጠውን ፡ ከመቀበል ፡ ሊከለከል ፡ አይገባውም ። እንደ ፡ ሕግ ፡ ፍርድ ፡ ዋስነቱ ፡ እውነተኛ ፡ ካልሆነ ፡ ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ ከዋሱ ፡ መክፈል ፡ አይገባም ።

፩ሺ.፺ ዋስ ፡ የሆኑት ፡ ሰው ፡ ቢሞት ፡ ገንዘብ ፡ ካለው ፡ እርሱን ፡ በተዋሰበት ፡ ከወራሾቹ ፡ መጠየቅ ፡ ለዋሱ ፡ ይገባዋል ። ዋሱ ፡ ቢሞትም ፡ ገንዘብ ፡ ያለው ፡ ከሆነ ፡ ለዋስ ፡ እነዚ ፡ ከወራሾቹ ፡ መጠየቅ ፡ ይገባዋል ። ገንዘብ ፡ ባይኖረው ፡ ግን ፡ ዋስ ፡ ካልሆነው ፡ አይፈልግ ።

፩ሺ.፺፩ የነፍስ ፡ መድኅንም ፡ መድን ፡ የሆነበትን ፡ ያመጣ ፡ ዘንድ ፡ ይገባዋል ፡ የይህች ፡ መድንነት ነገርም ፡ እገሌን ፡ ለእገሌ ፡ ለማድረስ ፡ ወይም ፡ በእገሌ ፡ ፊት ፡ ለእገሌ ፡ መድን ፡ ሁኛለሁ ። ወይም ፡ የእገሌ ፡ መድንነት ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ እንዲል ፡ ይሁን በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ የታ ወቀ ፡ ቀጠሮ ፡ ቢወስን ፡ ቀጠሮው ፡ በደረሰ ፡ ጊዜና ፡ መድን ፡ የሆነለትን ፡ ከእርሱ ፡ በሚፈል ግበት ፡ ጊዜ ፡ መድን ፡ የሆነውን ፡ በማናቸውም ጊዜ ፡ ፍለጋን ፡ ይፈላለጉት ። ቀጠሮው ፡ ሳይደ ርስ ፡ በዓለ ፡ ዕዳዉን ፡ መያዝ ፡ በተቻለው ፡ ጊዜ ቢያቀርበው ፡ ከዕዳዉ ፡ ዳነ ። ራሱንም ፡ ለባለ ዕዳዉ ፡ ቢያሳልፍ ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። ከተወሰ ነው ፡ ቀጠሮ ፡ በኋላ ፡ ባይገኝም ፡ እስኪያመ ጣው ፡ ድረስ ፡ ዳኛ ፡ የቀን ፡ ቀጠሮ ፡ ይሰጠው ። ከቀጠሮውም ፡ በኋላ ፡ ባያመጣው ፡ ፊቱን ፡ ለማ ቅረብ ፡ ብቻ ፡ የተዋሰው ፡ ከሆነ ፡ እርሱን ፡ በማ ድረስ ፡ ብቻ ፡ ይያዛል ። እርሱ ፡ እንደሆነ ፡ ቢስ

ተሰነአወ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ወውእቱ ፡ እመ ፡
ኢያብጽሐ ፡ በጊዜ ፡ ኀሠሣሁ ፡ ውእቱ ፡ ተሐበየ
ስዳ ፡ ዘላስሌሁ ፡ ወከዋኒሁ ፡ ከመዝ ፡ ወከመዝ ፡
ይከውን ፡ እምውእቱ ፡ ጊዜ ፡ ተሐብዩ ፡ ዘን
ዋይ ።

፩ሺ.፲፪ ወለእመ ፡ ኢተረክበ ፡ መድኅን ፡ ወተድኅኖ ፡
ለዘተድኅነ ፡ ካልእ ፡ መድኅን ፡ ወለዘሰ ፡ ዘቦቱ
መድኅን ፡ ይደሉ ፡ ተኀሥሦ ፡ በእንቲአሁ ፡
ወኢይደሉ ፡ ተድኅኖቱ ፡ ለዘይደሉ ፡ ላዕሌሁ ፡
ቀትል ፡ ወለእመ ፡ ሞተ ፡ ዘተድኅነሂ ፡ ይትኀ
ሠሡ ፡ አድኅኖቶ ፡ እመድኅን ፡ ወዘይደሉሰ ፡
ከመ ፡ ይኅሥሥ ፡ ቅድመ ፡ ለበዓለ ፡ ስዱሁ ፡
ወለእመ ፡ ኢረከቦ ፡ ይኅሥሥ ፡ ለመድኅን ።
፩ሺ.፲፫ ረስጠጅ ፡ ዘ፲ወ፬ቱ ፡ ወኢይደልዎ ፡ ለካህን ፡
ከመ ፡ ይትወሐስ ፡ ፩ደዪ ፡ ወየኀዝ ፡ ንዋየ ።
ዘኒቅያ ፡ ፲ወ፰ቱ ፡ ወለብእሲትኒ ፡ ኢይትወ
ከፉ ፡ እምኔሃ ፡ መድኅን ፡ ወኢተሐብዮ ።
፩ሺ.፲፬ ወዘሰ ፡ ይከውን ፡ በጽሕፈት ፡ አው ፡ በተአምኖ
ባሕቲቱ ፡ ወእመ ፡ ይክሕድ ፡ ተለቃሒ ፡ ዘተለ
ቅሐ ፡ ይትኀሠሥዎ ፡ በመሐላ ። ወለእመ ፡
መሐለ ፡ ወቆመ ፡ ቦቱ ፡ ሰማዕት ፡ እምድኅረ
ዝንቱ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ መጽሐፍ ፡ መጽሐፈ ፡
ዚአሁ ፡ ውእቱ ፡ ይኩን ፡ ፍትሑ ፡ ፍትሐ ፡
ዘክሕደ ፡ በዓለ ፡ ስዱሁ ፡ ወመሐለ ፡ ሎቱ ፡
ወባሕቱ ፡ እቅደምነ ፡ በዝንቱ ፡ አንቀጽ ፡
ቀዳማዊ ። ወእመሰ ፡ ኢመሐለ ፡ ይሰወ ፡ ላዕ
ሌሁ ፡ ዘተነግረ ፡ በጽሕፈቱ ፡ ወለእመ ፡ ኢኮነ ፡
ጽሕፈት ፡ እዴሁ ፡ ወትሕበቱ ፡ ይጼውዮ ፡
ለተለቃሒ ።
፩ሺ.፲፭ ወአእምሮ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አስተዓ
ቀበ ፡ እምበዓለ ፡ ስዱ ፡ ከመ ፡ ኢያሕምሞ ፡ ለበ
ዓለ ፡ ስዱሁ ፡ ሶበ ፡ ኀዮአ ፡ በከሊኦቱ ፡ ልብሰ ፡
ዚአሁ ፡ ዘእኁዝ ፡ በከመ ፡ ተብህለ ፡ በኦሪት ።
ወከልእ ፡ እምተኀሥሦቱ ፡ ኪያሁ ፡ ወገሠጾ ፡
ኢየአኀዞ ፡ ወኢያሕምሞ ፡ ላዕሌሁ ፡ በከመ ፡
ተነግረ ፡ በወንጌል ፡ በዝንቱ ፡ አንቀጽ ፡ ወበእ
ንቱ ፡ ዝንቱ ፡ ኢይደሉ ፡ አሕምሞ ፡ ላዕለ ፡
ጽንስ ። ወባሕቱ ፡ ለዘሀለወ ፡ ላዕሌሁ ፡ ልቃሕ ፡
በከዊነ ፡ ስድማ ፡ ኢይትኀሠሥዎ ፡ በእንቲ
አሃ ፡ ዘእንበለ ፡ በጊዜ ፡ ዘይደሉ ። ወለእመ ፡
ፈርሀ ፡ በእንቲአሁ ፡ የሀብዎ ፡ ዋሕሰ ፡ በትእ
ዛዘ ፡ ፈታሒ ።
፩ሺ.፲፮ ወለእመ ፡ ቦ ፡ ምንትኒ ፡ ዘይትኀሠሥዎ ፡ ባቲ ፡



ማማ ፡ በተፈለገም ፡ ጊዜ ፡ ባያቀርብ ፡ ሰዳዉን ፡
የራሱ ፡ አድርጎ ፡ ተዋሰ ። ሁኔታውም ፡ የገን
ዘብ ፡ ዋስ ፡ ከሆነበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እንደዚሁ፡
ይሆናል ።

፩ሺ.፲፪ መድኑ ፡ ባይገኝ ፡ ለመድኑ ፡ ሌላ ፡ መድን ፡
ቢሆነው ፡ መድን ፡ ላለው ፡ ሁሉ ፡ ስለእርሱ ፡
መፈላለግ ፡ ይገባል ። ሞት ፡ ለሚገባው ፡ መድን
መሆን ፡ አይገባም ። መድን ፡ የሆኑት ፡ ሰው ፡
ቢሞት ፡ ከመድኑ ፡ እርሱን ፡ ማዳን ፡ ይፈልጉ ፡
አስቀድሞ ፡ ሊፈልግ ፡ የሚገባውስ ፡ ባለዕዳ
ውን ፡ ነው ። ባያገኘው ፡ መድኑን ፡ ይፈልገው ።

፩ሺ.፲፫ ረስጠጅ ፡ ፲፬ ። ካህን ፡ ለአንድ ፡ ሰውስ ፡ እንኳ፡
ሊዋስ ፡ የእደራ ፡ ገንዘብም ፡ ሊይዝ ፡ አይገባ
ውም ። ኒቅያ ፡ ፲፰ ። ሴትንም ፡ በመድንነትና ፡
በዋስትና ፡ አይቀበሉ ።
፩ሺ.፲፬ በጽሕፈት ፡ ወይም ፡ በእምነት ፡ ብቻ ፡ የሚ
ሆን ፡ ግን ፡ ተበዳሪ ፡ የተበደረውን ፡ ቢክድ ፡
በመሐላ ፡ ይፈላለጉት ። ቢምል ፡ ከእዚህ ፡
በኋላ ፡ ጽሕፈቱ ፡ የእርሱ ፡ ጽሕፈት ፡ እንደ
ሆነ ፡ ምስክሮች ፡ ቢመሰክሩበት ፡ ፍርዱ ፡ ባለ
ሰዳዉን ፡ ክዶ ፡ እንደማለ ፡ ሰው ፡ ፍርድ ፡ ይ
ሁን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከመጀመሪያው ፡ አንቀጽ ፡
አስቀድመን ፡ ተናግረናል ። ባይምል ፡ ግን ፡
በደብዳቤው ፡ የተነገረው ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡
ተገባ ። የእጁ ፡ ጽሕፈት ፡ ዋስትናውም ፡ ባይ
ሆን ፡ ተበዳሪውን ፡ ይጥራው ።

፩ሺ.፲፭ በኦሪት ፡ እንደተነገረ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ያሲያዘውን፡
ልብሱን ፡ በመከልከል ፡ ተበዳሪን ፡ እንዳያስጨ
ንቀው ፡ እግዚአብሔር ፡ ባለዕዳን ፡ እንዳሰጠ
በቀ ፡ እወቅ ። (ዘጸ ፡ ፳፬ ፡ ፲ - ፲፭) ። እርሱንም ፡
ከመያዝ ፡ ከለከለው ። እንዳይዘው ፡ ክፉም ፡
እንዳያደርግበት ፡ ገሠጸው ። በወንጌል ፡ በመጀ
መሪያው ፡ አንቀጽ ፡ እንደተነገረ ። (ማቴ ፡ ፲፰ ፡
፴፪) ። ስለዚህ ፡ በችግረኛ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ መሥ
ራት ፡ አይገባም ። ነገር ፡ ግን ፡ ጊዜን ፡ በመወ
ሰን ፡ ብድር ፡ ያለበትን ፡ ሰው ፡ በሚገባው ፡
ጊዜ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ስለእርሱዋ ፡ አይፈላለ
ጉት ። ስለእርሱ ፡ ቢፈሩ ፡ በዳኛ ፡ ትእዛዝ ፡ ዋስ፡
ያስጠሩት ።
፩ሺ.፲፮ በእርሷ ፡ የሚፈላለጉት ፡ አንዳች ፡ ነገር ፡ ቢኖር፡

ወሰአልዎ ፡ ለመኰንን ፡ ሰብአ ፡ ዕዳሁ ፡ ከመ ፡ ይወስን ፡ ላዕሌሁ ፡ ለይ.ወስን ፡ ወለእመኒ ፡ ሜጠ ይሚጥ ፡ በእደ ፡ ዘየአምኖ ፡ ዘተረክበ ፡ እምጥ ሪቱ ፡ በቅድሜሆሙ ፡ ወበቅድመ ፡ ሰብአ ፡ ዕዳሁ ። አው ፡ በቅድመ ፡ መድኅኑ ፡ ወመድ ኅኖሙ ፡ ሚጡ ፡ በሰናይ ፡ በጽሕቅ ። ወያቅ ድሙ ፡ ሠይጦቶ ፡ ለዘይ.ማስን ፡ ፍጡነ ፡ ወእ ምዝ ፡ በእንስሳ ፡ አው ፡ በአብያት ፡ ሰለኵሉ ፡ ግብር ፡ ውስተ ፡ ምሥያጥ ፡ በቅድመ ፡ ሰብእ ።

፩ሺ.፲፯ ወኢይፍዲ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘተበውቀ ፡ ጥያቄሁ ፡ በሰ ማዕታት ፡ ወኢያብጽሕ ፡ በነገረ ፡ ሰዳውያን ፡ ባሕቲቶሙ ፡ እስከ ፡ ይከውን ፡ ተዓቅቦቱ ፡ እምተኃይለቶሙ ፡ ወኢይበቍዖ ፡ ተአምኖቱ ፡ ዘለቅሕዎ ፡ ባሕቲቱ ፡ ወይፍርሁ ፡ እምተኃ ይሎ ፡ ወይፍልጡ ፡ ቦቱ ፡ ዘይከውኖ ፡ ለመፍ ቅድ ፡ ዘከማሁ ። ለእመ ፡ ኢፈጸመ ፡ ንዋዩ ፡ ፈድየ ፡ ልቃሑ ፡ ይክፍልዎሙ ፡ በአምጣነ ፡ ንዋዩ ።

፩ሺ.፲፰ ወሰዘሂ ፡ ተረክበ ፡ ሐሳበ ፡ ንዋዩ ፡ በአም ጣነ ፡ ሜጡ ፡ የሀብዎ ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ሜጠ ፡ ኪያሁ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ሜጡ ፡ በውእቱ ፡ ጊዜ ፡ ብዙኀ ፡ የሀብዎ ፡ ዘይብዝኀ ። ወሰእመ ፡ ኢተረክበ ፡ ለቶቱ ፡ ንዋይ ፡ ወነገረ ፡ ተጽ ናሰ ፡ ዚአሁ ፡ ወአጠየቀ ፡ ሰብአ ፡ ዕዳሁ ፡ በእፈ ፡ እሰ ፡ የእምሩ ፡ ህላዌሁ ፡ ከመ ፡ በሐ ሰት ፡ ተናገረ ፡ ይሞቅሕ ፡ ሎሙ ፡ እስከ ፡ ይፈ ድዮሙ ። ወለእመ ፡ ፈቀዱ ፡ እምሕሎቶ ፡ ያምሕልዎ ፡ ወያኅድግዎ ። ወሰእመ ፡ ተጠየቀ ፡ ተጽናሱ ፡ በ፪ቱ ፡ ሰማዕት ፡ ዘየእምሩ ፡ ግብሮ ፡ ያጽንሕዎ ፡ እስከ ፡ የኀልፍ ፡ ተጽናሱ ። ወለ እመ ፡ ኮነት ፡ ሎቱ ፡ ዓስብ ፡ ይሥርዑ ፡ ላዕ ሌሁ ፡ ምጣኔ ፡ ዚአሁ ፡ እምድኅረ ፡ ነሚአ ፡ ዘየ አክሎ ። ወለእመ ፡ ኢተጠየቀ ፡ ተጽናሰ ፡ ዚአሁ ይደኅር ፡ እኅድኅቱ ።



ባለዕዳዎችም ፡ በእርሱ ፡ ይወስን ፡ ዘንድ ፡ ዳኛ ውን ፡ ቢጠይቁት ፡ ይወሰን ። ቢሸጥም ፡ ከገን ዘቡ ፡ የተገኘውን ፡ በእርሱና ፡ በባለዕዳዎቹ ፡ ፊት ፡ ወይም ፡ በመድኑና ፡ በመድኖቻቸው ፡ ፊት ፡ በሚያምነው ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ይሽጥ ። ሺያ ጩም ፡ በትክክል ፡ በትጋት ፡ ይሁን ። ፈጥኖ ፡ የሚበላሸውን ፡ ሺያጭ ፡ ያስቀድሙ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እንስሳውን ፡ ወይም ፡ ቤቱን ፡ ሰየሥ ራው ፡ ሁሉ ፡ በገበያ ፡ በሰዎች ፡ ፊት ፡ ይሁን ።

፩ሺ.፲፯ እርግጡ ፡ በምስክር ፡ ካልታወቀ ፡ በቀር ፡ አይከ ፈል ። ከተንኮላቸው ፡ መጠበቅ ፡ እስከሚሆንበት ድረስ ፡ በባለዕዳዎቹ ፡ ቃል ፡ እያቀርብ ። ያበደ ሩትን ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ማመን ፡ አይጠቅምም ። ከቅሚያም ፡ ወገን ፡ ይፍሩ ። እንደዚሁም ፡ ለመ ፍቅድ ፡ የሚሆነውን ፡ ለእርሱ ፡ ይለዩ ። ገንዘቡ፡ ብድሩን ፡ ሊከፍል ፡ ባይችል ፡ እንደ ፡ ገንዘቡ ፡ መጠን ፡ ያካፍልዋቸው ።

፩ሺ.፲፰ የገንዘቡ ፡ ሂሳብ ፡ በዋጋው ፡ ልክ ፡ ሰተገኘለት ፡ ሰው ፡ እርሱን ፡ የሸጠባትን ፡ ይሰጡት ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ዋጋው ፡ ብዙ ፡ ቢሆን ፡ የሚበዛውን ፡ ይስ ጡት ፡ ገንዘብ ፡ ባይገኝለት ፡ ችግሩንም ፡ ቢና ገር ፡ ባለዕዳዎቹ ፡ በሐሰት ፡ እንደተናገረ ፡ ኑሮ ውን ፡ በሚያውቁ ፡ አፍ ፡ ቢያስመሰክሩ ፡ እስከ ሚከፍላቸው ፡ ድረስ ፡ ይሠርላቸው ። ሊያም ሉት ፡ ቢወዱም ፡ አምለው ፡ ይተዉት ። ችግሩ ፡ ኑሮውን ፡ በሚያውቁ ፡ በሁለት ፡ ምስክሮች ፡ ቢረጋገጥ ፡ ችግሩ ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ ይጠ ብቁት ። ደመወዝ ፡ ብትኖረው ፡ የሚበቃውን ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ልኩን ፡ ይወ ስኑ ። ችግሩ ፡ ባይረጋገጥ ፡ መለቀቁ ፡ ይቀራል ።

## አንቀጽ ፹ወ፱ቱ ።

በእንተ ፡ ሕስት ።

፩ሺ.፲፱ ሕስትሰ ፡ ነሚአ ፡ በቍዔት ፡ ውእቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ቢዛ ፡ በገጽ ፡ እሙር ። መጽ ፡ ዘ፳ወ፬ቱ ፡ ትቢ ፡ ዘ፲ወ፩ዱ ፡ ወለእመ ፡ ቦ ፡ ዘተወሐሰ ፡ እንስሳ ፡ እስከ ፡ መካን ፡ ውሱን ፡ ወተዓደወ ፡ ኪያሁ ፡

## አንቀጽ ፡ ፹፱ ።

ስለትውስት ፡ ይናገራል ።

፩ሺ.፲፱ ትውሰትስ ፡ በታወቀ ፡ ቦታ ፡ ያለዋጋ ፡ ጥቅም ፡ ማግኘት ፡ ነው ። መጽ ፡ ፳፬ ። ትቢ ፡ ፲፩ ። እስከ ፡ ተወሰነ ፡ ቦታ ፡ ከብት ፡ የተዋሰ ፡ ቢኖር ፡ የተወሰነውን ፡ ቢያልፍ ፡ ከጕዳት ፡ ወገን ፡ ያገ

አንቀጽ ፡ ፳፱ ።

ኵሉ ፡ ዘያረክብ ፡ እምሕሠማት ፡ አው ፡ ሞተት፡ ይደልዎ ፡ ሰዳ ። ወእመኒ ፡ ኢዐደወ ፡ ወኮነ ፡ ዘረከባ ፡ በሀኬተ ፡ ዚአሁ ፡ አው ፡ በመግቦቱ ፡ ይደልዎ ፡ ሰዳ ። ወእመሰ ፡ ኢኮነ ፡ ከማሁ ፡ አው ሀሰወ ፡ እግዚአ ፡ ምስሌሁ ፡ ኢይደልዎ ፡ ሰዳ ። ወለእመ ፡ ኮነት ፡ በሀሰብ ፡ ወጠፍአት ፡ ይከ ውን ፡ ጥፍአታ ፡ በዓሰበ ፡ ዚአሃ ። ወለእመ ፡ ተዐደወ ፡ እመካን ፡ ዘተወሰነ ፡ የሀብ ፡ ለአው ሓሲ ፡ ተውሳከ ፡ ዓሰቡ ፡ በዘተዐደወ ።

፩ሺ.፰ ወኵሉ ፡ ዘይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይሥራዕ ፡ ቦቱ ፡ ውስተ ፡ ንዋዩ ፡ ይደልዎ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ያው ሕስ ፡ ኵሎ ፡ ንዋዮ ፡ ዘይሠርዕ ፡ ቦቱ ፡ ከመ ፡ ያውሕስ ፡ ኵሎ ፡ ዘይከውኖ ፡ ለበቍዔት ፡ በዓ ሰቡ ፡ ምስለ ፡ ዳኅናሁ ፡ ወሰቅበተ ፡ ርእሱ ። ወይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይንሣእ ፡ ሤጠ ፡ ዚአሁ ፡ ለዘጠፍአ ፡ እምኔሁ ፡ በሰሌተ ፡ ጥፍአቱ ፡ ለእመ ፡ ተዐደወ ፡ ላዕሌሁ ፡ ውስቱ ። እመ ፡ ኮነ ፡ እምእንስሳ ፡ ውእቱ ፡ ወሞተ ፡ አው ፡ ጐየ፡ ኢይረክቦ ፡ ሰዳ ፡ ዘእንበለ ፡ ዳእሙ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘወሀበ ፡ ተሐባዪ ፡ ለእግብአቱ ፡ ድኅነ በኵሉ ። ወለእመ ፡ ተገአዘ ፡ ይኩን ፡ በከመ ፡ ቃሉ ፡ ለየውሓሲ ፡ ምስለ ፡ መሐላው ። ወእመ ፡ አኮ ፡ ሠናይ ፡ ከመ ፡ ኢትትወሐስ ፡ ሕሰተ ፡ ወኢተአኅዝ ፡ አኅዘ ፡ ወኢትትሀሰብ ፡ ዘእን በለ ፡ በትእዛዘ ፡ አውሓሲ ፡ በዕድሜ ፡ ዘተወ ሰነ ።

፩ሺ.፰፩ ወለአውሓሲ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ያግብእ ፡ ንዋዮ ጊዜ ፡ ፈቀደ ፡ ዘእንበለ ፡ ይኩን ፡ ዘቀደመ ፡ ወሰኖ ፡ አው ፡ ዘተሠርዐ ፡ ጊዜሁ ፡ አው ፡ ኢተ ፈጸመት ፡ ንሢአ ፡ በቍዔት ፡ ባቲ ። ወኢትትሀ ቀብ ፡ ዓይኑ ፡ ምስለ ፡ በቍዔታት ፡ ዘባቲ ፡ ዘከመ ፡ ዲናራት ፡ ወጠፋልሐ ፡ ብሩር ፡ ወዘይ ሰፈር ፡ ወይትሜዘን ፡ ልቃሕ ፡ ውእቱ ፡ ወአኮ ፡ ሕሰት ።

ስለ ፡ አደራ ።

ኛት ፡ ሁሉ ፡ ወይም ፡ ብትሞት ፡ ሰዳ ፡ (መክ ፈል) ፡ ይገባዋል ። ባያልፍ ፡ ጉዳት ፡ ያገኛትም ፡ በሰንፍናው ፡ ወይም ፡ ባመጋገቡ ፡ ቢሆን ፡ ሰዳ ፡ ይገባዋል ። እንዲህ ፡ ባይሆን ፡ ግን ፡ ወይም ፡ ጌታዋ ፡ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ ቢዋሽ ፡ ሰዳ ፡ አይገባ ውም ። በክሬዶ ፡ ቢሆን ፡ ብትጠፋ ፡ ጥፋቷ ፡ በዋጋዋ ፡ ይሆናል ። ከተወሰነ ፡ ቦታ ፡ ቢያልፍ፡ በተላለፈበት ፡ የኪራዩን ፡ ጭማሪ ፡ ለአዋሰው ፡ ይስጥ ።

፩ሺ.፰ በገንዘቡ ይሠራበት ዘንድ የሚገባው ሰው ፡ ሁሉ ፡ ያውስ ፡ ዘንድ ፡ የሚያዝዝበት ፡ ገንዘቡን ሁሉ ፡ ከዓይነቱና ፡ ራሱ ፡ ከመጠበቅ ፡ ጋር ፡ በኪራዩ ፡ ለጥቅም ፡ የሚሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ሊያ ሲዝ ፡ ይገባዋል ። ከተወሰነው ፡ በላይ ፡ ጨምሮ፡ ቢተላለፍ ፡ በጠፋበት ፡ ቀን ፡ የጠፋውን ፡ ዋጋ ፡ ከእርሱ ፡ ሊቀበል ፡ ይገባዋል ። ከእንስሳ ፡ ወገን ፡ ቢሆን ፡ ቢሞት ፡ ወይም ፡ ቢጠፋ ፡ ሰዳ ፡ አያገኘውም ። በሁሉ ፡ ደኅና ፡ አድርጎ ፡ ለመመለስ ፡ ዋስ ፡ የጠራ ፡ ቢሆን ፡ ነው ፡ እንጂ፡ ቢከራከሩ ፡ ከመሐላው ፡ ጋራ ፡ እንደአዋሹ ፡ ቃል ፡ ይሁን ። ያም ፡ ባይሆን ፡ በተወሰነ ፡ ቀን ፡ ያለአዋሹ ፡ ትእዛዝ ፡ ትውስት ፡ ባትዋስ ፡ መያዣ ፡ ባትይዝ ፡ ባትከራይ ፡ መልካም ፡ ነው ።

፩ሺ.፰፩ ለሚያውስ ፡ ሰው ፡ የቀደመ ፡ ውሳኔ ፡ ወይም ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ሳይደርስ ፡ ወይም ፡ በእርሷ ፡ ጥቅምን ፡ ማግኘቱ ፡ ካልተፈጸመች ፡ በወ ደደው ፡ ጊዜ ፡ ገንዘቡን ፡ ሊመልስ ፡ ይገባዋል ። ዓይነቷ ፡ በእርሷ ፡ ከሚገኙ ፡ ጥቅሞች ፡ ጋር፡ አትጠባበቅ ። ይኸውም ፡ እንደ ፡ ዲናር ፡ እንደ ተመዘነ ፡ ብር ፡ እንደሚሰፈር ፡ እንደሚመዘን ፡ ያለ ፡ ብድር ፡ ነው ። ትውስት ፡ ግን ፡ አይደለም ።

## አንቀጽ ፡ ፳ወ፱ቱ ።

በእንተ ፡ ማኅፀንት ።

፩ሺ.፰፪ ጠሰ ፡ ፲ወ፰ቱ ፡ ወነተሉ ፡ ዘተወሰከ ፡ ላዕሌሁ ። ማኅፀንትሰ ፡ ንዋይ ፡ ይእቲ ፡ ዘይሁብ ፡ እማን ዓኒ ፡ ለዘያማኅፅኖ ፡ ከመ ፡ ይዕቀብ ፡ ሎቱ ፡ ዘእ ንበለ ፡ ካዕበት ፡ እምኔሁ ፡ ጊዜ ፡ አግብእታ ።

## አንቀጽ ፡ ፳፱ ።

ስለ ፡ አደራ ፡ ይናገራል ።

፩ሺ.፰፪ ጠሰ ፡ ፲፰ ። ሁሉም ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ የተጨመረ ነው ። አደራስ ፡ ከእርሱ ፡ በሚመልሳት ፡ ጊዜ ፡ ያለትርፍ ፡ ይጠብቅለት ፡ ዘንድ ፡ አደራ ፡ ባይ ፡ ለአደራ ፡ ተቀባይ ፡ የሚሰጣት ፡ ገንዘብ ፡ ናት ።

ወይእቲኬ ፡ እምነት ፡ ዘአማኅፃኒሃ ፡ ዘያነብራ ፡ ኀበ ፡ ዘያማኅፅኖ ። ወለዘሂ ፡ ተወክፋ ፡ ይደልዎ፡ ከመ ፡ ይዕቀባ ፡ በዕበይ ፡ ጻሕቅ ፡ ወይኩን ፡ በቀ በተ ፡ ኪያሃ ፡ ከመ ፡ ንዋዩ ። ወለእመ ፡ ጠፍአት ፡ እምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ እልቦቱ ፡ ዕዳ ። ወለእመ ፡ ፈቀደ ፡ እግብእታ ፡ ለእግዚእ ፡ እንዘ ፡ ዳኅን ፡ ይእቲ ፡ በጊዜ ፡ ግብአታ ፡ ወአበየ ፡ ነሚአታ ፡ ይእተ ፡ ጊዜ ፡ ለእመ ፡ ጠፍአት ፡ ወማሰንት ፡ ማሰኖ ፡ ፍጥረታዊ ፡ ዘከመ ፡ እንስሳ ፡ መዋቲ ፡ እው ፡ ምንትኒ ፡ ዘያማስን ፡ በቍንቍኔ ፡ እው ፡ ተንሥእ ፡ ላዕሌሃ ፡ ዘኢይትከሀሎ ፡ ከመ ፡ ይሰ ድዶ ፡ ዘከመ ፡ ውዕየት ፡ በእሳት ፡ እው ፡ ተሠጥሞ ፡ እው ፡ ተበርብሮ ፡ እው ፡ ሰረቅ ፡ እው ፡ ትዕግልት ፡ ኢይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይፍዲ ፡ ለእመ ፡ ኢተዐውቀ ፡ በስምዐ ፡ ጥዩቀ ፡ ከመ ፡ ኮነ ፡ ዝንቱ ፡ እምትሕሉቱ ፡ ወእከየ ፡ ምግ ብናሁ ፡ ወኢዓቀቦቱ ፡ ላቲ ፡ ከመ ፡ ንዋዩ ፡ እሰመ ፡ ለዛቲ ፡ ግብር ፡ ይደሉ ፡ ተኃሥሦ ፡ በእንቲአሃ ፡ ወእመኒ ፡ ኮነ ፡ ዘእቅደመ ፡ ሠረዐ ፡ ውሳኔ ፡ በእንቲአሃ ፡ በተሰናእዎቶሙ ። ወለእመ ኀሠሣ ፡ እግዚእ ፡ ወከልእ ፡ እምኔሁ ፡ ወው እቱ ፡ እንዘ ፡ ይክል ፡ መጥዎታ ፡ ሎቱ ፡ አው ፡ ክሕደ ፡ ኪያሃ ፡ ወኀበአ ፡ አምነ ፡ ባቲ ፡ ይፍዲ ፡ ኪያሃ ።

፩ሺ.፳፫ ወለእመኒ ፡ አስተዋፅአ ፡ በተለቅሖ ፡ ለነፍሱ ፡ አው ፡ ለካልኡ ፡ እው ፡ በተዓስቦ ፡ ካልአን ፡ እው ፡ በእኅዝ ፡ እው ፡ በውሕስት ፡ በስሒተ ፡ ተወሐሲ ፡ አው ፡ ይትሐበዩ ፡ ከመ ፡ ያግብእ ፡ ኪያሃ ፡ ኀበ ፡ ምዕቅብናሁ ፡ ለዘወሀቦ ፡ ኪያሃ ። ወለእመሂ ፡ ወሀባ ፡ ማኅፀንተ ፡ ለካልኡ ፡ ዘእን በለ ፡ እመክንዮ ፡ በሐዊረ ፡ ፍኖት ፡ እው ፡ በካ ልእ ፡ ይትሐበይ ፡ ኪያሃ ፡ እስከ ፡ ያገብእ ። ወኢ ይደልዎ ፡ ለዳግማዊ ፡ ከመ ፡ ይመጥዋ ፡ ለእግ ዚእ ፡ ዘእንበለ ፡ በትእዛዙ ፡ ለአማኅፃኒሃ ፡ ሎቱ፡ ወበቃለ ፡ ዚእሁ ፡ ገጸ ፡ በገጽ ፡ አው ፡ በመልእ ክቱ ፡ እመኒ ፡ በሐዋርያሁ ፡ አው ፡ በጽሒፈ ፡ መልእክት ፡ እምርት ፡ እንተ ፡ ትነግር ፡ ጥዩቀ ፡ ትእምርት ።

፩ሺ.፳፬ ወኢይደሉ ፡ ለዘእማኅፀኑ ፡ ኀቤሁ ፡ ከመ ፡ ይእ በይ ፡ እመጽሐፍ ፡ ዘአመጋቢ ፡ ዘትነግር ፡ ከመ፡ ማኅፀንት ፡ ሀለወት ፡ ኀቤሁ ፡ ወኢብውሕ ፡



ያህችውም ፡ ካደራ ፡ ተቀባይ ፡ ዘንድ ፡ የሚያኖ ራት ፡ ያደራ ፡ አስቀማጭ ፡ እምነት ፡ ናት ። ለተቀበላትም ፡ ሰው ፡ በታላቅ ፡ ትጋት ፡ ሊጠ ብቃት ፡ ይገባዋል ። እርሷን ፡ መጠበቁም ፡ እንደ ፡ ገንዘቡ ፡ ይሁን ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ብት ጠፋ ፡ ዕዳ ፡ የለበትም ። በምትመለሰበት ፡ ጊዜ ፡ ደኅና ፡ ሳለች ፡ ለባለቤቷ ፡ ሊመልስለት ፡ ቢ ወድ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ መቀበሏን ፡ እንቢ ፡ ቢል ፡ ያንጊዜ ፡ ባሕርያዊ ፡ መጥፋትን ፡ ፈጽማ ፡ ብት ጠፋ ፡ ይኸውም ፡ እንደሚች ፡ ከብት ፡ ወይም ፡ ነቀዝ ፡ እንደሚያበላሸው ፡ ማናቸውም ፡ ነገር ፡ ቢሆን ፡ ነው ። ወይም ፡ ሊከላከልለት ፡ የማይቻ ለው ፡ ነገር ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ቢነሣ ፡ ይኸውም ፡ በእሳት ፡ እንደመቃጠል ፡ ወይም ፡ እንደመስ ጠም ፡ ወይም ፡ እንደመዘረፍ ፡ ወይም ፡ እንደመ ሰረቅ ፡ ወይም ፡ እንደመቀማት ፡ ቢሆን ፡ ይህ ፡ ከተንኰሉ ፡ ከመጋገቡ ፡ ክፋት ፡ እንደገንዘቡም፡ እድርጎ ፡ ካለመጠበቁ ፡ የተነሣ ፡ እንደሆነ ፡ በማስረጃ ፡ ምስክር ፡ ካልታወቀ ፡ ዕዳ ፡ መክ ፈል ፡ አይገባውም ። ለዚች ፡ ሥራ ፡ ስለእርሱ ፡ መመራመር ፡ ይገባልና ። ስለእርሱ ፡ በመስማ ማታቸው ፡ ውሳኔ ፡ መወሰንን ፡ ያስቀደመ ፡ ካልሆነ ፡ ጌታዋ ፡ ቢፈልጋትም ፡ ከእርሱ ፡ ቢከ ለክለው ፡ ይኸውም ፡ ለእርሱ ፡ እርሷን ፡ መስ ጠት ፡ ሲቻለው ፡ ወይም ፡ እርሷን ፡ ቢክድ ፡ መልሶም ፡ ቢያምን ፡ እርሷን ፡ ይክፈል ።

፩ሺ.፳፫ ለራሱ ፡ ወይም ፡ ለሌላው ፡ በመበደር ፡ ወይም ፡ ለሌሎች ፡ በማከራየት ፡ ወይም ፡ በማያገባ ፡ በተዋሰው ፡ ዋጋ ፡ በውስት ፡ ወይም ፡ እርሷን ፡ ወደሰጠው ፡ ሰው ፡ እደራነት ፡ እርሷን ፡ ሊመ ልስ ፡ ይዋሳት ፡ ዘንድ ፡ ቢያወጣጣት ፡ መን ገድ ፡ በመሄድ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሳያመካኝ ፡ ለሌላው ፡ አደራ ፡ ቢሰጣትም ፡ እርሷን ፡ እስኪ መልስ ፡ ድረስ ፡ ዋስ ፡ ይጥራ ። ለሁለተኛውም ፡ ለእርሱ ፡ አደራ ፡ በሰጠው ፡ ሰው ፡ ትእዛዝና ፡ በቃሉ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ወይም ፡ በደብዳቤው ፡ በመልእክተኛውም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ የመልእ ክቱን ፡ እርግጠኛነት ፡ የምትናገር ፡ የታወቀች ፡ ደብዳቤ ፡ በመጻፍ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ለጌታዋ ፡ ሊሰጥ ፡ አይገባውም ።

፩ሺ.፳፬ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ አደራ ፡ ለአስቀመጡበት ፡ ሰው ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ አደራ ፡ እንዳለች ፡ ከምትናገር ፡ ከአደራ ፡ አስጠባቂ ፡ ደብዳቤ ፡ የተ

ለዘያነብር ፡ ማኅፀንተ ፡ ኅቤሁ ፡ ከመ ፡ ይእበዮ፡ እጽሕፎተ ፡ ማኅፀንት ፡ ዘይሁብዎ ፡ ዘትንግር ፡ ከመ ፡ ኅቤሁ ፡ ሀለወት ።

፩ሺ፰፻፬ ወለእመ ፡ አዘዘ ፡ ወሃቢ ፡ ማኅፀንት ፡ ከመ ፡ ኢያውፅአ ፡ ወእውፅአ ፡ እው ፡ አዘዞ ፡ ከመ ፡ የሀባ ፡ ለእገሌ ፡ ወኢወሀባ ፡ ሎቱ ፡ እው ፡ አዘዞ ፡ ከመ ፡ ኢይመጥዋ ፡ ለካልእ ፡ በጥዩቅ ፡ ወመጠዋ ፡ ሎቱ ፡ እው ፡ አዘዞ ፡ ከመ ፡ ያንብራ ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ እሙር ፡ ወከመ ፡ ኢያንብራ ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ እንሌያዊ ፡ ወእበዮ ፡ ወኢኮነ ፡ እመንገለ ፡ ዓጸባ ፡ ዘከሠት ፡ ዘኢይትከሀሎ ፡ አንብሮታ ፡ ይትእኀዝ ፡ በዕዳሃ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘወረሳ ፡ እምኀበ ፡ ዘነበረት ፡ ኅቤሁ ማኅፀንት ፡ ወአእመረ ፡ ባቲ ፡ ወተከሀሎ ፡ ከመ፡ ይገብራ ፡ ለእግዚእ ፡ ወኢገብራ ፡ ሎቱ ፡ ይትእኀዝ ፡ በዕዳሃ ።

፩ሺ፰፻፭ ወእመኒ ፡ ፈቀደ ፡ ነጊደ ፡ ርኁቀ ፡ ብሔረ ፡ ወኢረከቦ ፡ ለእግዚእ ፡ ወኢለመጋቢሁ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ የሀባ ፡ ለፈታሒ ፡ ወእመ ፡ ኢተከሀሎ ፡ ለብእሲ ፡ ምእመን ፡ ወለእመ ፡ ኢረከበ ፡ ለእግዚእ ፡ ማኅፀንት ፡ ይጸንሖ ፡ እስከ ፡ ሰዶሚ ፡ መዋዕል ፡ ዘኢየሐዩ ፡ ከማሁ ፡ እምድኅሬሃ ። ወእምዝ ፡ የሀባ ፡ ለወራስያኒሁ ፡ ወለእመ ፡ እልቦቱ ፡ ወራስያን ፡ ትእዛዝ ፡ ለመሥዋዕት ፡ ወይመጽውትዋ ፡ በእንቲአሁ ፡ በፍና ፡ ጽድቅ ። እመሂ ፡ በኑልቈ ፡ እው ፡ በመጽውቶ ፡ በእንቲአሁ ፡ በትእዛዘ ፡ ፈታሒ ፡ እው ፡ በሰማዕት ።

፩ሺ፰፻፮ ወይደልዎ ፡ ለእማኅፃኒ ፡ ወለዘእማኅፀኑ ፡ ኅቤሁ ፡ ሥኡረ ፡ ማኅፀንት ፡ ጊዜ ፡ ፈቀደ ፡ ኅበ፡ ዘይትከሀሎ ፡ ለዘእማኅፀኑ ፡ ኅቤሁ ፡ ከመ ፡ የሀቦ ፡ ኪያሃ ፡ ወለእማኅፃኒ ፡ ከመ ፡ ይትመጠዋ ። ወለእመ ፡ እበየ ፡ ዘንተ ፡ ትከውን ፡ ዕዳ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወወፅአት ፡ ዕዳ ፡ እምተሐባዪ ፡ ካልእ ።

፩ሺ፰፻፯ ወለዘሂ ፡ እስተጋብእዎ ፡ እማኅፀንት ፡ ለእስርሮ ፡ እው ፡ ዘይመስሎ ፡ ለዝንቱ ፡ ወፍትሑኒ ፡ ይኩን ፡ ከመ ፡ ነሚእ ፡ ማኅፀንት ። ወለኮሰ ፡ ዘኮነ ፡ እማኅፀንት ፡ እምሳለ ፡ ዘይረብሳ ፡ እው ፡ ዘኮነ ፡ ወዘይመስሎ ፡ ለዝንቱ ፡ ወፍትሑኒ ፡ ከመ ፡ ነሚእ ፡ ማኅፀንት ፡ በእንብሮ ፡ ፈታሒ ።

፩ሺ፰፻፰ ወዘሂ ፡ ተወክፈ ፡ ማኅፀንተ ፡ በእግዚእ ፡ ወተመ



ነሣ ፡ እንቢ ፡ ሊል ፡ አይገባውም ። በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ አደራ ፡ ለሚያኖር ፡ ሰው ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ እንዳለች ፡ የምትናገር ፡ የሚሰጡትን ፡ አደራ ፡ ማስጻፍ ፡ እንቢ ፡ ሊል ፡ አይገባም ።

፩ሺ፰፻፬ አደራ ፡ ሰጭ ፡ እንዳያወጣት ፡ ቢያዝዝ ፡ ቢያወጣት ፡ ወይም ፡ ለእገሌ ፡ እንዲሰጥ ፡ ቢያዝዘው ፡ ለእርሱም ፡ ባይሰጥ ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ እንዳይሰጥ ፡ በእርግጥ ፡ ቢያዘው ፡ ለእርሱም ፡ ቢሰጣት ፡ ወይም ፡ ከታወቀ ፡ ቦታ ፡ ያኖራት ፡ ዘንድ ፡ እገሌ ፡ በሚባል ፡ ቦታ ፡ ውስጥ ፡ እንዳያስቀምጣት ፡ ቢያዝዘው ፡ እንቢም ፡ ቢለው ፡ እርሷን ፡ ማኖር ፡ ከማይቻለው ፡ ከተገለጠ ፡ ጭንቅ ወገን ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በዕዳዋ ፡ ይያዛል ። አደራ ፡ ከተቀመጠችበት ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ የወረሳት ፡ ቢሆን ፡ እርሷን ፡ ቢያውቅ፡ ለጌታዋ ፡ መንገር ፡ ሲቻለው ፡ ለእርሱ ፡ ባይነግረው ፡ በዕዳዋ ፡ ይያዛል ።

፩ሺ፰፻፭ ወደሩቅ ፡ አገር ፡ ሊሄድ ፡ ወደዶ ፡ ጌታዋን ፡ ወይም ፡ አስተዳዳሪውን ፡ ባያገኘው ፡ ለዳኛ ፡ ሊሰጣት ፡ ይገባዋል ። ባይቻለውም ፡ ለታመነ ፡ ሰው ፡ ይስጥ ። ያደራውን ፡ ባለቤት ፡ ባያገኘው ፡ ከእርሷ ፡ በኋላ ፡ እንደእርሱ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ እስከማ ይኖርበት ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ይጠብቀው ። ከዚያ፡ በኋላ ፡ ለወራሾቹ ፡ ይስጣት ። ወራሾች ፡ ባይኖሩት ፡ ትእዛዝ ፡ ለመሥዋዕት ፡ ነው ። (ለመሥዋዕት ፡ ይታዘዝ) ፡ ስለእርሱ ፡ በጽድቅ ፡ መንገድ ፡ ይመጽውቷት ። በመቍለትም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ በመመጽወት ፡ ስለእርሱ ፡ በዳኛ ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ በምስክሮች ፡ ይሁን ።

፩ሺ፰፻፮ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ አደራ ፡ ያስቀመጡበት ፡ ሰው ፡ በሚቻለው ፡ ገንዘብ ፡ እርሷን ፡ ይስጥ ፡ ዘንድ ፡ አደራ ፡ አስቀማጭም ፡ ይቀበላት ፡ ዘንድ ፡ በወደደ ፡ ጊዜ ፡ ለአደራ ፡ አስቀማጭና ፡ አደራ ፡ ላስቀመጡበትም ፡ ሰው ፡ አደራውን ፡ መሻር ፡ ይገባዋል ። ይህን ፡ እንቢ ፡ ቢል ፡ ዕዳ ፡ ትሆን በታለች ። ዕዳም ፡ ከሌላው ፡ ዋስ ፡ ወጣች ።

፩ሺ፰፻፯ ለማረፍ ፡ ካደራው ፡ የሰበሰበት ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የሚመስለው ፡ ፍርዱ ፡ አደራን ፡ እንደ ፡ መቀበል ፡ ይሁን ። ከአደራ ፡ ወገን ፡ የሚረባውን ፡ የመሰለ ፡ ወይም ፡ የሆነው ፡ ይህንም ፡ የመሰለው ፡ ሁሉ ፡ ፍርዱም ፡ በዳኛ ፡ ቢት ፡ አደራ ፡ እንደማኖር ፡ ነው ።

፩ሺ፰፻፰ አደራን ፡ ከጌታዋ ፡ የተቀበለ ፡ ሰው ፡ ከመል

ጠዋ ፡ እምእደ ፡ ሐዋርያሁ ፡ እግዚእ ፡ ውእቱ ፡ አማኅፃኒሁ ፡ ወሎቱ ፡ የዐቢ ፡ ወአኮ ፡ ለሐዋርያሁ ፡ ዘእንበለ ፡ በትእዛዙ ፡ ወእመኒ ፡ ሞተ ፡ ትኩን ፡ ለወራሲያኒሁ ። ወዘኒ ፡ ተወክፈ ፡ ማኅፀንተ ፡ እምዕዱ ፡ ወይቤሎ ፡ ከመ ፡ ይመጥዋ ፡ ለካልኡ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይመጥዋ ፡ ለዝኩ ፡ ካልእ ፡ ወይጠይቆ ፡ ከመ ፡ ይእቲ ፡ ማኅፀንት ፡ ወአኮ ፡ ከመ ፡ የዐቢ ፡ ለአማኅፃኒሁ ፡ በእዴሁ ፡ ለካልኡ ።

፩ሺ፴ ወለእመ ፡ እንበሩ ፡ ፪ቱ ፡ ማኅፀንተ ፡ ኀበ ፡ ፩ዱ ፡ ኢይደልዎ ፡ መጠውዎታ ፡ ለ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘእንበለ ፡ በሥምረተ ፡ ካልኡ ።

፩ሺ፴፩ ወለዘኒ ፡ ወሀብዎ ፡ ማኅፀንተ ፡ እመኒ ፡ ገብረ ፡ አው ፡ እንስሳ ፡ ወኢወሀበሙ ፡ ሲሳየ ፡ ወኢስቴ ፡ እስከ ፡ ይመውቱ ፡ ይትኣኀዝ ፡ በሰዳሆሙ ። ወእመኒ ፡ ኮነ ፡ ይቤሎ ፡ ዘአማኅፀኖ ፡ ኢተሀቦሙ ፡ መብልዐ ፡ ወስቴ ፡ ወነገሮ ፡ በወሀቦሙ ፡ እምንዋዩ ፡ ለመፍቅዶሙ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይትኀሠሥ ፡ ኪያሁ ፡ እምበዓለ ፡ ማኅፀንት ። ወለእመ ፡ ከልአ ፡ ትኩዎን ፡ ኀቤሁ ፡ ከመ ፡ እንተ ፡ አኀዘ ፡ በእምሳን ፡ ዘወሀበ ፡ ወትወለአ ፡ እምተሐብዮቱ ፡ በውእቱ ፡ ጊዜ ፡ ወይኩን ፡ በከመ ፡ ቃሉ ፡ ለዘወሀብዎ ፡ ማኅፀንተ ፡ ምስለ ፡ መሐላሁ ። ወእምከመ ፡ ተገአዘ ፡ በእንተ ፡ ማኅፀንት ፡ ወተፈደየ ፡ ሰዳ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ተአመና ፡ በንዋዩ ፡ ወለእመ ፡ አምጽአ ፡ አማኅፃኒ ፡ ስምዐ ፡ ጥዩቀ ፡ ይኩን ፡ በከመ ፡ ቃሉ ።

፩ሺ፴፪ ወኢይደሉ ፡ ውሂበ ፡ ማኅፀንት ፡ ዘእንበለ ፡ ለዘያለምዶ ፡ ከዊነ ፡ እስተዋስኦ ፡ ወንጊሥተ ፡ በዓሉ ፡ ለተቀብሎቱ ፡ ንዋዩ ፡ እምድኅረ ፡ ለመደ ፡ እስተዋስኦ ፡ ወተወክፎ ።

፩ሺ፴፫ ወትበጥል ፡ ማኅፀንት ፡ በሞቱ ፡ ለዘአንበሮሙ ፡ ኀቤሁ ፡ ወለዘአኀዞ ፡ ጋኔን ፡ እስከ ፡ ይሌቡ ።

፩ሺ፴፬ ወዘኒ ፡ ተወክፈ ፡ ማኅፀንተ ፡ ወእምዝ ፡ አእመረ ፡ ከመ ፡ አማኅፃኒሁ ፡ ሰረቃ ፡ አው ፡ ተዓገላ ፡ በኀይል ፡ ይደሉ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይትልውዎ ፡ በካሰበት ። ወዘኢያስተሐመመ ፡ በንዋየ ፡ ማኅፀንት ፡ በከመ ፡ ያስተሐምም ፡ በንዋዩ ፡ ናሁ ፡ ተኃሕለወ ፡ ወይትኃሠሥ ፡ አማኅፃኒ ፡ ከመ ፡ ትሕሳዊ ፡ ወጽንዐ ፡ ሕሊና ፡ ወተሀይዮ ፡ ዘእንበለ ፡ ይኩን ፡ ስንእወ ፡ ናሁ ፡ ኮነት ፡ ላዕለ ፡ ንዋይ ፡ ካልኣት ፡ ግብር ።

እክተኛውም ፡ እጅ ፡ የወሰዳት ፡ ጊታዋ ፡ አደራ ፡ ባዩ ፡ ነው ። ለእርሱ ፡ ይስጠው ፡ እንጂ ፡ እርሱ ፡ ካላዘዘ ፡ በቀር ፡ ለመልእክተኛው ፡ አይደለም ። ቢሞትም ፡ ለወራሾቹ ፡ ትሁን ። ከአንዱ ፡ አደራ ፡ የተቀበለ ፡ ለሌላም ፡ ስጥልኝ ፡ ቢለው ፡ ለዚያ ፡ ለሌላው ፡ ሊሰጣት ፡ ይገባዋል ። ይህችውም ፡ አደራ ፡ እንደሆነች ፡ ያስረዳው ። በሌላው ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ለአደራ ፡ አስጠባቂዋ ፡ ሊሰጥ ፡ አይደለም ።

፩ሺ፴ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ከአንድ ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ አደራ፡ ቢያኖሩ ፡ ሁለተኛው ፡ ካልፈቀደ ፡ በቀር ፡ ከእነርሱ ፡ ለአንደኛው ፡ መስጠት ፡ አይገባውም ።

፩ሺ፴፩ አደራ ፡ የሰጡት ፡ ሰው ፡ ባሪያም ፡ ቢሆን ፡ ከብትም ፡ ቢሆን ፡ እስኪሞቱ ፡ ድረስ ፡ ምግብና ፡ መጠጥ ፡ ባይሰጣቸው ፡ በሰዳቸው ፡ ይያዛል ። አደራ ፡ የሰጠው ፡ ምግብ ፡ መጠጥ ፡ አትስጣቸው ፡ ያለው ፡ ቢሆን ፡ ለመፍቅዳቸው ፡ ከገንዘቡ ፡ የሰጣቸውን ፡ ሁሉ ፡ ከባለአደራው ፡ እርሱን ፡ ሊፈልግ ፡ ይገባዋል ። ቢከለከል ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ በሰጠው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ እንደመያዣ ፡ ትሆናለች ። ያንጊዜም ፡ ከዋስነቱ ፡ ትወጣለች ። ስለአደራውና ፡ ሰዳን ፡ ስለመክፈል ፡ ቢማሉ ፡ ከመሐላው ፡ ጋር ፡ አደራ ፡ እንዳስጠበቁት ፡ ሰው ፡ ቃል ፡ ይሁን ። እርሱ ፡ በገንዘብ ፡ እምኖታልና ። አደራ ፡ አስቀማጭ ፡ የሚያስረዳ ፡ ምስክር ፡ ቢያመጣ ፡ እንደ ፡ ቃሉ ፡ ይሁን ።

፩ሺ፴፪ ማውጣትና ፡ መቀበልን ፡ ከለመደ ፡ በኋላ ፡ ገንዘቡን ፡ ለመቀበል ፡ የማውጣጣትና ፡ ከባለቤቱም ፡ የመፈላለግ ፡ ሁኔታን ፡ ለለመደ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አደራ ፡ መስጠት ፡ አይገባም ።

፩ሺ፴፫ አደራ ፡ የአስቀመጡበት ፡ ሰው ፡ ቢሞት ፡ ጋኔን፡ የያዘውም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ እአምሮው ፡ እስኪመለስ ፡ ድረስ ፡ አደራ ፡ ትፈርሳለች ።

፩ሺ፴፬ አደራ ፡ የተቀበለውም ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አደራ ፡ አስቀማጩ ፡ እንደሰረቃት ፡ ወይም ፡ በኀይል ፡ እንደቀማት ፡ ቢያውቅ ፡ በአጠፋፏ ፡ ሊከታተሉት ፡ ይገባል ። ለገንዘቡ ፡ እንደሚተጋ ለአደራውም ፡ ገንዘብ ፡ የማይተጋ ፡ እነሆ ፡ ተንኮል ፡ ሥራ ፡ የተስማማ ፡ ሳይሆን ፡ ከዳተኛ ፡ ጨካኝ ፡ ቸልተኛ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ አደራ ፡ አስቀማጩ ፡ ይፈላለገው ። እነሆ ፡ በገንዘብ ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ ግብር ፡ አለች ።

## አንቀጽ ፡ ፴ ።

### በእንተ ፡ ምግብና ።

፩ሺ.፴፫ እምቀኖና ፡ ነገሥት ፡ ወምክር ፡ ዘበእንቲአሃ ። መክ ፡ ፶ወ፮፡ ፡ ዘ፷ወ፩ዱ ፡ ፷ወ፭፡ ፡ ፻ወ፫፡ ፡ ፻ወ፳ ። ወዘተሉ ፡ ዘአሠነየ ፡ ሥርዓታ ፡ ለነፍሱ፡ በምንትኒ ፡ ግብር ፡ እምግብራት ፡ ወፍትሐታት ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ መጋቢ ፡ በላዕሌሆሙ ። ወምግብናሰ ፡ ትከውን ፡ ብውሕተ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ግብራት ፡ ወፍትሐታት ፡ ወትትአመን ፡ በንዋይ ፡ ጥዩቅ ፡ ዘእንበለ ፡ ካልኡ ፡ ወይትዌከፉ ፡ መጋቢ ፡ በዓስብ ፡ ወዘእንበለ ፡ ዓስብ ። ወሶበ ፡ ተሐጕለ ፡ ንዋየ ፡ አመጋቢ ፡ በእደ ፡ መጋቢ ፡ ዘእንበለ ፡ ጽልሑት ፡ ወኢሀኬት ፡ ኢይደልዎ ፡ ይፍዲ ። ወኢይቀውም ፡ ምግብና ፡ ዘእንበለ ፡ በአብሖተ ፡ ቃሉ ፡ ለአመጋቢ ፡ ወተወክፎተ ፡ ቃሉ ፡ ለመጋቢ ፡ አው ፡ በግቢር ።

፩ሺ.፴፬ ወኢይደልዎ ፡ ለመጋቢ ፡ ከመ ፡ ይሢጥ ፡ ምንተኒ ፡ ንዋየ ፡ በስደ'ሜ ፡ ለእመ ፡ ኢአዘዘ ፡ አመጋቢ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ በዘንቱ ፡ እመኒ ፡ በብዙኅ ፡ አው ፡ በዘየሐጽጽ ፡ እምሤጡ ። ወለእመ፡ ይቤሎ ፡ ሢጥ ፡ሊተ ፡ በስደ'ሜ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ይሢጣ ፡ በፍጡን ፡ እመ ፡ ኢነትጉ ፡ ሤጡ ፡ በእንተ ፡ ክዊኖቱ ፡ ፍጡን ።

፩ሺ.፴፭ ወኢይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይማየጥ ፡ ለአመጋቢሁ ፡ ምንተኒ ፡ እምንዋየ ፡ ብሩር ፡ ካልእ ፡ እምዘ ፡ አዘዘ ፡ በቃሉ ፡ አው ፡ በመልእክቱ ። ወለእመ ፡ ይቤሎ ፡ ተማየጥ ፡ ሊተ ፡ በ፲፻ት ፡ ፍጡን ፡ ይደልዎ ፡ በስደ'ሜ ፡ ከመ ፡ ይማየጥ ፡ በ፲፻ት ። ወለእመ ፡ አኀዘ ፡ እምዘተማየጠ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ያግብእ ፡ ለአመጋቢሁ ፡ ለዘቦቱ ፡ ነውር ፡ እንዘ ፡ ቦ ፡ በእደዊሁ ። ወለእመሰ ፡ መጠዎ ፡ ለአመጋቢሁ ፡ ኢይሚጣ ፡ ካዕበ ፡ ኀቤሁ ፡ ዘእንበለ ፡ በትእዛዙ ።

፩ሺ.፴፮ ወለእመ ፡ ይቤሎ ፡ ተማየጥ ፡ ሊተ ፡ በንዋይከ ፡ አው ፡ እምዘ ፡ ዚአከ ፡ ዘይትተ ፡ በ፲፻ት ፡ ወአንሃ ፡ አፈድየከ ፡ በጊዜ ፡ ዘይመጽእ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይማየጥ ፡ ሎቱ ። ወይኩን ፡ ዘይት ፡ ለአመጋቢ ፡ ወይትመጠወ ፡ ቦቱ ፡ እምድኅረ ፡ አወፈየ ፡ ሤጠ ፡ ዚአሁ ፡ ወ፲፻ት ፡ ይኩን ፡ ለመጋቢ ፡ ለእመ ፡ በጽሐ ፡ ጊዜሁ ፡ ወይኩን ፡ ቅብአ ፡

## አንቀጽ ፡ ፴ ።

### ስለ ፡ ምግብና ፡ (ስለአስተዳደር) ፡ ይናገራል) ።

፩ሺ.፴፫ ከፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ስለእርሷም ፡ ከተነገረው ፡ ምክር ፡ የተገኘ ፡ ነው ። መክ ፡ ፶፮ ፡ ፷፩ ፡ ፷፭ ፡ ፻፫ ፡ ፻፳ ። ከሥራና ፡ ከፍርድ ፡ በማናቸውም ፡ ሥራ ፡ የራሱን ፡ ሥርዓት ፡ ያሳመረ ፡ ሁሉ ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ መጋቢ ፡ (አስተዳዳሪ) ፡ ሊሆን ፡ ይገባዋል ። አስተዳዳርስ ፡ በሥራዎችና ፡ በፍርዶች ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ የተገባች ፡ ትሆናለች ። ከሌላው ፡ በቀር ፡ በተረጋገጠ ፡ ገንዘብ ፡ ትታመናለች፡ መጋቢ ፡ በገንዘብ ፡ ያለገንዘብ ፡ ይቀበላታል ፡ ያለተንኮልና ፡ ያለስንፍና ፡ የአመጋቢ ፡ ገንዘብ፡ በመጋቢ ፡ እጅ ፡ ቢጠፋ ፡ ሊከፍል ፡ አይገባውም ። ምግብና ፡ በአመጋቢ ፡ ፈቃድና ፡ በመጋቢ ፡ ቃል ፡ መቀበል ፡ ወይም ፡ በሥራ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አይጸናም ።

፩ሺ.፴፬ አመጋቢ ፡ በብዙም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ከዋጋው፡ በሚያንስ ፡ በዚህ ፡ እንዲሆን ፡ ካላዘዘ ፡ በቀር ፡ ለመጋቢው ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ (በዱቤ) ፡ ምንም ፡ ገንዘብ ፡ ይሸጥ ፡ ዘንድ ፡ አይገባውም ። በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ (በዱቤ) ፡ ሽጥልኝ ፡ ቢለው ፡ በችኮላ ፡ ስለሆነ ፡ ዋጋው ፡ ካልጎደለ ፡ ፈጥኖ ፡ ሊሸጣት ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ.፴፭ በቃሉ ፡ ወይም ፡ በመልእክቱ ፡ ካዘዘው ፡ ሌላ ፡ ከብር ፡ ገንዘብ ፡ ሌላ ፡ ለአመጋቢው ፡ ሊገዛለት ፡ አይገባውም ። ፈጥነህ ፡ በሽህ ፡ ብር ፡ ግዛልኝ ፡ ቢለው ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ በሽህ ፡ ብር ፡ ሊገዛ ፡ ይገባዋል ። ከገዛው ፡ ገንዘብ ፡ ቢይዝም ፡ በእጁ ፡ ሳለ ፡ ነውር ፡ ያለበትን ፡ ለአመጋቢው ፡ ሊመልስ ፡ ይገባዋል ። ለአመጋቢው ፡ ቢሰጠው ፡ ግን ፡ ካላዘዘ ፡ በቀር ፡ ዳግመኛ ፡ ወደእርሱ ፡ አይመልሳት ።

፩ሺ.፴፮ በገንዘብህ ፡ ወይም ፡ ከአንተ ፡ በሽህ ፡ ብር ፡ ዘይት ፡ ግዛልኝ ፡ እኔም ፡ በሚመጣው ፡ ጊዜ ፡ እከፍልሃለሁ ፡ ቢለው ፡ ሊገዛለት ፡ ይገባዋል ። ዋጋውን ፡ ከከፈለ ፡ በኋላ ፡ ዘይቱ ፡ ለአመጋቢው ፡ (ለጌታው) ፡ ይሁን ። ያስተዳድርበትም ። ጊዜው ፡ ከደረሰ ፡ ሽሁ ፡ ብር ፡ ለአስተዳዳሪው ፡ ይሁን ። የዘይቱ ፡ ቅባት ፡ ስለዋጋው ፡ ፈንታ ፡

ዘይትቀበል ፡ ታሕተ ፡ እዴሁ ፡ አንዘ ፡ ዘየንቲ ፡ ማሁ፡ ወለእመ ፡ ተማየጠ ፡ ሎቱ ፡ በንዋየ ፡ ዚአሁ ፡ ዘእንበለ ፡ የአዝዞ ፡ ይኩን ፡ እንዘ ፡ ታሕተ ፡ እዴሁ ።

፩ሺ፴፱ ወለእመኒ ፡ አመገቦ ፡ በተማይጦ ፡ ንዋዩ ፡ እመር ፡ ኢይደልዎ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይማየጦ ፡ ለንፍሱ ፡ ወለኮሉ ፡ ዘተማየጦ ፡ በስመ ፡ ዘአመገቦ ፡ ወፈድፋደሰ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ በንዋዩ ፡ ኢይደልዎ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይረስዮ ፡ ለንፍሱ ፡ ዘእንበለ ፡ በመባሕቱ ። ወኢይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይቀጽር ፡ ለአመጋቢሁ ፡ ውስተ ፡ ሥዩም ፡ በዘይወሕድ ፡ እምጊዜ ፡ ወኢበተማይጦ ፡ በዘይበዝኅ፡ እምኔሁ ፡ በጊዜ ፡ ወመካን ፡ ዘይከውን ፡ በውስቴቱ ፡ ተቃጽሮ ፡ ዘእንበለ ፡ በምዕኔ ፡ ዘተሰነአወ ፡ ቦቱ ፡ ምስለ ፡ ተማያጢ ፡ ወሠያጢ ፡ ዘከመ ፡ ተኀልፎት ፡ ማእከለ ፡ ቀመተ ፡ ማእምራን ፡ ፈድፋደሰ ፡ ተቃጽሮን ፡ ምስለ ፡ እሊአሁ ፡ ወወላዲሁ ፡ ወወልዱ ፡ ወወልደ ፡ ወልዱ፡ ወብእሲቱ ።

፩ሺ፵ ወዘወወበ ፡ ሎቱ ፡ አመጋቢሁ ፡ ፩ደ ፡ ዲናረ ፡ ከመ ፡ ይማየጥ ፡ ሎቱ ፡ ቦቱ ፡ አሐተ ፡ በግዕተ ፡ ወተማየጠ ፡ ሎቱ ፡ ቦቱ ፡ ፪ተ ፡ አባግዐተ ፡ ዘዘአሐቲ ፡ እምኔሆን ፡ ዘትከውን ፡ ፩ደ ፡ ዲናረ ፡ እማንቱ ፡ ይኩና ፡ ለአመጋቢሁ ። ወለእመ ፡ አመገቦ ፡ በሠይጥ ፡ ለብእሲ ፡ በሢጥ ፡ ሰፈሐ ፡ ወለእመ ፡ ኢኮነ ፡ መፍትዱ ፡ ዘእንበለ ፡ ሢጥ ፡ ባሕቲቱ ፡ ይለወ ፡ ሢጦ ፡ ለካልኡ ፡ በውእቱ ፡ ንዋይ ፡ እመ ፡ ኮነ ፡ ጥዩቀ ፡ በከዊነ ፡ ሢጥ ።

፩ሺ፵፩ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ተጋእዞ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ስምዐ ፡ ይኩን ፡ በከመ ፡ ቃሉ ፡ ለመጋቢ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ነዋ ፡ ተአመኖ ፡ ላዕለ ፡ ንዋዩ ። ለእመ፡ ፈደየ ፡ ዕዳ ፡ ዘየንቲ ፡ አመጋቢሁ ፡ እንዘ ፡ ኢሀሎ ፡ ውእቱ ፡ ወኢያስምዐ ፡ ላዕለ ፡ በዓለ ፡ ዕዳ ፡ ወእምዝ ፡ ክሕዶ ፡ ውእቱ ፡ በዓለ ፡ ዕዳ ፡ ይደልዎ ፡ ዕዳ ። ወለእመኒ ፡ አማኅፀኖ ፡ መጋቢሁ ፡ ንዋየ ፡ ኀበ ፡ ካልእ ፡ ያስምዕ ፡ ለስማዕት፡ ቦቱ ፡ ለአመጋቢሁ ፡ ዘአማኅፀኖ ።

፩ሺ፵፪ ወለእመ ፡ ተመገበ ፡ ፩ዱ ፡ ብእሲ ፡ ለ፪ቱ ፡ እደው ፡ በንዋይ ፡ ኢይደልዎ ፡ ለ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ከመ ፡ ይትገበር ፡ ውስቴቱ ፡ በባሕቲቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ አምሳለ ፡ አግዕዞ ፡ ግብር ፡ ዘእንበለ ፡ ኑሚአ ፡ ቤዛ ፡ ዘየንቲቱ ፡ ወኢትእዛዝ ፡ ዘእንበለ ፡ አማኅጸኒሁ ፡ ኅቤሁ ፡



በመያዣነት ፡ በእጁ ፡ ይሁን ። ሳያዘው ፡ በገንዘቡ ፡ ቢገዛለት ፡ በእጁ ፡ የተያዘ ፡ ይሁን ።

፩ሺ፴፱ በታወቀ ፡ ገንዘብ ፡ ግዥ ፡ መጋቢ ፡ ቢያደርገው፡ ለራሱ ፡ ሊገዛው ፡ አይገባውም ። በአመገበው ፡ ስም ፡ የገዛውን ፡ ሁሉ ፡ ይልቁንም ፡ በገንዘቡ ፡ ቢሆን ፡ በፈቃዱ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ለራሱ ፡ ሊያደርገው ፡ አይገባውም ። በሚሸጠው ፡ ከዋጋው ፡ በሚያንስ ፡ በመግዛትም ፡ ከእርሱ ፡ (ከዋጋው ፡) በሚበዛ ፡ በውስጡ ፡ መቆጣጠር ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜና ፡ ቦታ ፡ ለመጋቢው ፡ ሊቆጣጠር ፡ አይገባውም ። ከገዢና ፡ ከሻጭ ፡ ጋራ ፡ በተስማማበት ፡ ልክ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ያኸውም ፡ በአዋቂዎች ፡ ውሳኔ ፡ መካከል ፡ እንደ መተላለፍ ፡ ያለ ፡ ነው ። ይልቁንም ፡ ከወገኖቹ ፡ ጋራ ፡ ያሉ ፡ አባቱና ፡ ልጁ ፡ የወንድ ፡ ልጁ ፡ ልጅና ፡ ሚስቱ ፡ ተቆጣጣሪዎች ፡ ናቸው ።

፩ሺ፵ መጋቢው ፡ አንዲት ፡ በግ ፡ ይገዛለት ፡ ዘንድ ፡ ፩ ፡ ዲናር ፡ የሰጠው ፡ ሰው ፡ ከእነርሱ ፡ እያንዳንዷ ፡ አንዳንድ ፡ ዲናር ፡ የምትሆን ፡ ፪ ፡ በጎች ፡ በዚያ ፡ ቢገዛለት ፡ እነዚያ ፡ ለአመጋቢው ፡ ይሁኑ። በታወቀ ፡ ዋጋ ፡ ለሰው ፡ በመሸጥ ፡ መጋቢ ፡ ቢያደርገው ፡ ፈቃዱ ፡ ያለዋጋ ፡ ብቻ ፡ ካልሆነ ፡ በዋጋ ፡ ሁኔታ ፡ የተረጋገጠ ፡ ከሆነ ፡ በዚያው ፡ ገንዘብ ፡ (ዋጋ) ፡ ዋጋው ፡ ለሌላው ፡ ተገባው ።

፩ሺ፵፩ ምስክር ፡ የሌለበት ፡ ክርክር ፡ ቢሆን ፡ እንደመጋቢው ፡ ቃል ፡ ይሁን ። እነሆ ፡ እርሱ ፡ በገንዘቡ ፡ አምኖታልና ። እርሱ ፡ ሳይኖር ፡ በአመጋቢው ፡ ፈንታ ፡ ዕዳ ፡ ቢከፍል ፡ ለባለዕዳውም ፡ ባያሰማ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ባለዕዳው ፡ ቢክድ ፡ ዕዳ ፡ ይገባዋል ። መጋቢው ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ ገንዘብ ፡ አደራ ፡ ቢያኖር ፡ አደራ ፡ ያስቀመጠው ፡ ገንዘብ ፡ ለአመጋቢው ፡ እንደሆነ ፡ ለምስክር ፡ ያሰማ ።

፩ሺ፵፪ አንድ ፡ ሰው ፡ ለሁለት ፡ ሰዎች ፡ በገንዘብ ፡ መጋቢ ፡ ቢሆን ፡ ከእነርሱ ፡ ለአንዱ ፡ ብቻውን፡ ሊሠራበት ፡ አይገባውም ። ስለእርሱ ፡ ፈንታ ፡ ዋጋ ፡ ያለመቀበል ፡ ባሪያን ፡ ነፃ ፡ ማውጣትን ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ያለ ፡ አስቀማጭው ፡ ከሌለ ፡ ወይም ፡

እው ፡ ፈጽሞ ፡ ዕዳ ፡ ዘላዕሌሁ ።

፩ሺ.፺፫ ወዘተማየጠ ፡ ገብረ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይገዝኦ ፡ ዘንተ ፡ ውስተ ፡ መጽሐፍ ፡ ዘተማየጠ ። ወኢይደልዎ ፡ ለመጋቢ ፡ ከመ ፡ ያመግብ ፡ ላዕለ ፡ ዘእመገብዎ ፡ ባቲ ፡ ዘእንበለ ፡ ትእዛዘ ፡ እመጋቢሁ ፡ እው ፡ ከመ ፡ ይብጻሕ ፡ ወኢይክል እዎ ፡ እው ፡ በእንተ ፡ ዓጸባ ፡ ከሡት ።

፩ሺ.፺፬ ወኢይፃእ ፡ ምግብና ፡ እመጋቢ ፡ ዘእንበለ ፡ በሥምረተ ፡ እመጋቢ ፡ ባሕቲቱ ፡ አላ ፡ እስከ ፡ ይብጽሕ ፡ ከዊን ፡ ወኢይወፅእ ፡ እምኔሃ ፡ በፈቃደ ፡ ርእሱ ፡ ዳእሙ ፡ እስከ ፡ የእምር ፡ እመጋቢሁ ፡ ወእስከ ፡ ያወፍዮ ፡ ከመ ፡ ይሥራዕ ፡ በንዋዩ ፡ እው ፡ ከመ ፡ ይርከብ ፡ መጋቢ ፡ ካልአ ፡ በአምሳሊሁ ፡ ወማእዜኒ ። ወእምከመ ፡ ወዕአ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ እምግብና ፡ ሥርዓት ፡ በሞት ፡ እው ፡ ለእመ ፡ ቦቱ ፡ መላኪ ፡ በላዕሌሁ ፡ ተሠዕረት ፡ ምግብናሁ ፡ ለእመ ፡ አእመረ ፡ ካልኡ ፡ አው ፡ ኢያእመረ ። ወለእመ ፡ ዐብደ ፡ መጋቢ ፡ ዕበደ ፡ ብዙኀ ፡ እው ፡ ስእነ ፡ ስኢነ ፡ ከሡተ ፡ በአምሳለ ፡ ዑረት ፡ ወዘይመስሎ ፡ በጠለት ፡ ለእመኒ ፡ አእመረ ፡ እመጋቢሁ ፡ እው ፡ ኢያእመረ ።

ዕዳ ፡ ከሌለበት ፡ ማዘዝ ፡ አይገባውም ።

፩ሺ.፺፫ ባሪያ ፡ የገዛ ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ የገዛውን ፡ በመጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ሊጽፈው ፡ ይገባዋል ። መጋቢ ፡ እርሱን ፡ መጋቢ ፡ በአደረጉባት ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ መጋቢ ፡ ሊሾም ፡ አይገባውም ። በአመጋቢው ፡ ትእዛዝ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ደርሶ ፡ እስኪመለስ ፡ ወይም ፡ በታወቀ ፡ ጭንቅ ፡ አይከልከሉት ።

፩ሺ.፺፬ ምግብና ፡ ያለ ፡ እመጋቢው ፡ ፈቃድ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ከመጋቢው ፡ አይውጣ ። ሁኔታው ፡ እስኪደርስ ፡ ድረስ ፡ ነው ፡ እንጂ ። በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ ከሹመቱ ፡ አይወጣም ። እመጋቢም ፡ እውቆ ፡ በገንዘቡ ፡ ይሠራበት ፡ ዘንድ ፡ እስኪሰጠው ፡ ድረስ ፡ ወይም ፡ በመሰሉ ፡ ሌላ ፡ መጋቢ ፡ እስኪያገኝ ፡ ድረስ ፡ መቸም ፡ መች ፡ ይቆይ ፡ እንጂ ። ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ በሞት ፡ ከምግብና ፡ ሥርዓት ፡ ቢወጣ ፡ ወይም ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ ገዢ ፡ ቢኖርበት ፡ ሌላው ፡ ቢያውቅም ፡ ባያውቅም ፡ ምግብናው ፡ ትቀራለች ። መጋቢው ብዙ ፡ ስንፍና ፡ ቢሰንፍ ፡ ወይም ፡ የተገለጸ ፡ ድካም ፡ ቢደክም ፡ መታወርና ፡ የመሰለውንም ፡ በመሰለ ፡ ነገር ፡ እመጋቢው ፡ ቢያውቅም ፡ ባያውቅም ፡ ምግብናው ፡ ትቀራለች ።

## አንቀጽ ፡ ፴ወ፮ዱ ።

በእንተ ፡ ግዕዛን ፡ ወግብርናት ፡ ወአግዓዝያን ።

፩ሺ.፺፭ ወመብዝኅቲኒ ፡ እምቀኖና ፡ ነገሥት ፡ ጠስ ፡ ዘ፴ወ፬ቱ ፡ መክ ፡ ዘ፴ወ፭ቱ ፡ ዘ፴ወ፯ቱ ፡ ዘ፴፯ቱ ፡ ዘ፺ወ፫ቱ ። ወዘተርፈሂ ፡ እምኔሁ ፡ በከመ ፍትሐ ፡ አእምሮ ፡ ውእቱ ፡ እስመ ፡ ኵሎሙ ፡ ሰብእ ፡ ሱቱፋን ፡ ውስተ ፡ ግዕዛን ፡ በሥርዐ ፡ ፍጥረታዊ ። ወዳእሙ ፡ ጸብእ ፡ ውኑይለ ፡ ፈረስ ፡ ታመጽእ ፡ በሙ ፡ ከመ ፡ ይትቀነዩ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ እስመ ፡ ሕገ ፡ ጸብእ ፡ ወመዊእ ፡ ትሬስዮሙ ፡ ለምዉኣን ፡ አግብርተ ፡ ለመዋኢያን ።

፩ሺ.፺፮ ወአሪትኒ ፡ ታጤይቅ ፡ ከመ ፡ ይቅንይዎሙ ፡ ለውፁኣን ፡ እምሃይማኖት ፡ ወዘሂ ፡ ተወልዱ ፡ እምኔሆሙ ። እስመ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስቴታ ፡ ዘይብል ፡ ይኩኑ ፡ ለክሙ ፡ አግብርተ ፡ ወአእማተ ፡

## አንቀጽ ፡ ፴፮ ።

ለለነፃነት ፡ ስለተገዥነት ፡ ስለ ፡ ነፃ ፡ አውጭዎችም ፡ ይናገራል ።

፩ሺ.፺፭ አብዛኛውም ፡ ከፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ የተገኘ ፡ ነው ። ጠስ ፡ ፴፬ ። መክ ፡ ፴፭ ። ፴፯ ፡ ፴፯ ፡ ፺፫ ። ከእርሱ ፡ የቀረውም ፡ እንደ ፡ አእምሮ ፡ ፍርድ ፡ (አስተያየት) ፡ ነው ። ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በጥንተ ፡ ተፈጥሮ ፡ በነፃነት ፡ አንድ ፡ ናቸውና ። መጣላትና ፡ የፈረስ ፡ ጉልበት ፡ እርስበርሳቸው ፡ ይገዙ ፡ ዘንድ ፡ (መገዛትን) ፡ ታመጣባቸዋለች ፡ እንጂ ። የጠብና ፡ የማቸነፍ ፡ ሕግ ፡ ድል ፡ የሆኑትን ፡ ድል ፡ ላደረጉት ፡ ባሮች ፡ (ተገዦች) ፡ ታደርጋቸዋለችና ።

፩ሺ.፺፮ ኦሪትም ፡ ከሃይማኖት ፡ የወጡትንና ፡ ከእነርሱም ፡ የተወለዱትን ፡ እንዲገዟቸው ፡ ታስረዳለች ። እንዲህ ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ በውስጧ ፡ አለና ። በዙሪያችሁ ፡ካሉ ፡ ከአሕዛብና ፡ አብረ

እለ ፡ ትነሥእዎሙ ፡ እምእሕዛብ ፡ እለ ፡ ይነ
ብሩ ፡ በዓውድክሙ ፡ ወእምነ ፡ ፈላስያን ፡ እለ ፡
ይነብሩ ፡ ምስሌክሙ ፡ ወእምኔሆሙ ፡ ተሣ
የጡ ፡ ወእምዘርእሙ ፡ ዘተወልደ ፡ ውስተ ፡
ምድርክሙ ፡ ወይኩኑ ፡ ለክሙ ፡ ዘትወርስ
ዎሙ ፡ ወለደቂቅክሙ ፡ እምድኅሬሆሙ ።

፩ሺ.፺፯ ወኢይደሉ ፡ ሠይጦ ፡ ገብር ፡ ምእመን ፡ ለዘኢየ
እምን ፡ ወውሉዱ ፡ ለገብር ፡ ምልክና ፡ ለመላ
ኪሆሙ ፡ እመኒ ፡ ተወልዱ ፡ እምአግዓዚት ፡
አው ፡ እምአመት ።

፩ሺ.፺፰ ወዘወልደ ፡ አመት ፡ ቅኔት ፡ ለመላኪሃ ፡ እመ ፡
ኮነ ፡ እምአግዓዚ ፡ አው ፡ እምገብር ፡ እመሂ ፡
በአውስቦ ፡ እው ፡ እምዝሙት ፡ ዘኢኮነ ፡ እም
እግዚአ ፡ ወለእመ ፡ ተግዕዘት ፡ እንዘ ፡ ዕንስት ፡
ይእቲ ፡ ውእቱኒ ፡ ዘውስተ ፡ ከርሣ ፡ ይከውን ፡
ግዑዘ ፡ በእንተ ፡ ዘኮነ ፡ መዋዕለ ፡ ፅንሳ ፡ ኪያሁ፡
እንዘ ፡ ግዕዝት ፡ ይእቲ ፡ ወይደሉ ፡ አግዕዞተ ፡
ዕኑስ ፡ ባሕቲቱ ፡ ዘእንበለ ፡ እንተ ፡ ፀንሰት ፡
ኪያሁ ፡ ወወልዳ ፡ ለአግዓዚት ፡ እምአግዓዚ ፡
አው ፡ ገብር ፡ ዘአግዓዝዎ ፡ ወእመኒ ፡ መለከዋ ፡
እምድኅረ ፡ ፀንሰት ፡ ኪያሁ ፡ ወእምቅድመ ፡
ትለዶ ፡ እስመ ፡ ለአግዓዚኒ ፡ ኢይዌስኩ ፡ ዲበ ፡
ግዕዛኑ ፡ ግብርናተ ፡ ካልኡ ።

፩ሺ.፺፱ ወአግዕዞስ ፡ እምግብረ ፡ ትሩፋት ፡ ይእቲ ፡ ድል
ዉት ፡ ከመ ፡ ይግበሩ ፡ ኪያሃ ፡ እስመ ፡ ምጽ
ዋት ፡ ትሩፋት ፡ ይእቲ ፡ ወአብሖተ ፡ ብእሲ ፡
ከመ ፡ ይምልክ ፡ ነፍሶ ፡ በፍትሕ ፡ ጥንተ ፡
ግዕዘ ፡ ጠባይዒሁ ፡ ወኢይትዐወቅ ፡ ጥይቁሁ ፡
ዘእንበለ ፡ በኀዲገ ፡ መላኪሁ ፡ ወእመኒ ፡ እግ
ዓዞ ፡ በካልእ ፡ ፍና ፡ ይደልዎ ፡ ግበ ፡ ዚአሁ ፡
እምቅድመ ፡ ፍጻሜሁ ፡ ወለእመ ፡ ተማየጦ ፡
ዳግመ ፡ ይበጽሎ ፡ ፍናዋት ፡ እስከ ፡ ይደግም ፡
ሐድሶቶሙ ፡ ወእመኒ ፡ እግዓዛ ፡ ለጊዜ ፡ ዘት
መጽእ ፡ ኢይደልዋ ፡ ቅንየት ፡ ዘእንበለ ፡
ዘትትለእኮ ፡ እስከ ፡ ጊዜ ፡ ኅዲጎታ ፡ ወእም
ኔሃ ፡ ባቲ ፡ ትእዛዝ ፡ ወኵሉ ፡ ዘተሰነአዋ ፡ እን
ቲእሃ ፡ ወእምነ ፡ ዘኢይትቀወማ ፡ ይደሉ ፡ ዝ ።
ወላለሊሁ ፡ ከመ ፡ ይትለአክ ፡ ለወልዱ ፡ እምድ
ኅረ ፡ ግዕዛኑ ፡ ዓመታተ ፡ እሙራተ ፡ ወአኮ ፡
ከመ ፡ ይጠስን ፡ ላዕሌሁ ፡ ወላዕለ ፡ ውሉዱ ፡
ከመ ፡ ይትቀነዩ ፡ ሎቱ ፡ ወለዘርእ ፡ እምጣነ ፡
ሀለወ ፡ ወይኩን ፡ ሎሙ ፡ ኵሉ ፡ ዘአጥረዩ ፡
እስመ ፡ ግብርናት ፡ ትከውን ፡ በዝንቱ ፡ ውሳኔ ።

ዋችሁ ፡ ከሚኖሩ ፡ ከስደተኞች ፡ የምትወስዷ
ቸው ፡ ለእናንተ ፡ ወንዶች ፡ ባሮችና ፡ ሴቶች ፡
ባሮች ፡ ይሁኗችሁ ። ከእነርሱ ፡ በሀገራችሁ ፡
ከተወለደ ፡ ከዘራቸውም ፡ ግዙ ። ለእናንተ ፡
ከእናንተም ፡ በኋላ ፡ ለልጆቻችሁ ፡ የምትወር
ሷቸው ፡ ይሁኑ ።

፩ሺ.፺፯ አማኒውን ፡ ባሪያ ፡ ላለመነ ፡ ሰው ፡ መሸጥ ፡
አይገባም ። የባሪያ ፡ ልጆቹ ፡ ለጌታ ፡ ገንዘቦች ፡
ናቸው ። ከእመቤት ፡ ወይም ፡ ከባሪያዪቱ ፡
ቢወለዱ ።

፩ሺ.፺፰ የሴት ፡ ባሪያ ፡ ልጅም ፡ ለጌትዋ ፡ ሊገዛ ፡ ይገ
ባል ። ከጌታ ፡ ወይም ፡ ከባሪያ ፡ የተወለደ ፡
ቢሆን ፡ በጋብቻ ፡ ወይም ፡ ከጌታዋ ፡ ያይደለ ፡
በዝሙት ፡ ቢሆን ፡ ፀንሳ ፡ ሳለች ፡ ነፃ ፡ ብት
ወጣ ፡ እርሱን ፡ የመፅነሷ ፡ ወራት ፡ ነፃ ፡ ሳለች ፡
ስለሆነ ፡ በሆዷ ፡ ያለውም ፡ ሕፃን ፡ ነፃ ፡ ይሆ
ናል ። እርሱን ፡ ከፀነሰችው ፡ በቀር ፡ የተፀነሰ
ውን ፡ ብቻ ፡ ነፃ ፡ ማውጣት ፡ ይገባል ። ከጨዋ፡
የተወለደ ፡ ነፃ ፡ የወጣች ፡ የባሪያ ፡ ልጅ ፡
ወይም ፡ ነፃ ፡ ያወጡት ፡ ባሪያ ፡ እርሱን ፡ ከፀነ
ሰችው ፡ በኋላ ፡ ሳትወልደው ፡ ቢገዟት ፡ ለጌ
ታም ፡ በነፃነቱ ፡ ላይ ፡ የሌላውን ፡ ተገዥነት ፡
አይጨምሩምና ።

፩ሺ.፺፱ ከትሩፋት ፡ ወገን ፡ የምትሆን ፡ ነፃ ፡ ማውጣትስ
እርሷን ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ የምትገባ ፡ ናት ።
ፍጹምት ፡ ምጽዋት ፡ ናትና ፡ ለሰው ፡ ሥል
ጣን ፡ መስጠትም ፡ በጥንታዊ ፡ የተፈጥሮው ፡
ጠባዩ ፡ ፍርድ ፡ ራሱን ፡ ይገዛ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።
በገዢው ፡ መተው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ዕርግጡ ፡
አይታወቅም ። በሌላ ፡ መንገድ ፡ ነፃ ፡ ቢያወ
ጣው ፡ ነፃ ፡ መውጣቱ ፡ ከመፈጸሙ ፡ አስቀ
ድሞ ፡ ዋጋው ፡ ይገባዋል ። ዳግመኛ ፡ ቢገዛው ፡
እነርሱን ፡ ማደስ ፡ እስኪደግም ፡ ድረስ ፡ ነገሮች
ይቀራሉ ፡ (ይፈርሳሉ) ፡ ለሚመጣው ፡ ጊዜ ፡
ነፃ ፡ ቢያወጣት ፡ እስከሚተዋት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡
ከምታገለግለው ፡ በቀር ፡ መገዛት ፡ አይገባ
ትም ። ከእርሷም ፡ ትእዛዝ ፡ አለባት ። የተሰ
ማማት ፡ ሁሉ ፡ የእርሷ ፡ ነው ። ከማይቃወ
ማትም ፡ ወገን ፡ ይህ ፡ ይገባል ። ከነፃነቱ ፡
በኋላ ፡ በታወቁ ፡ ዘመኖች ፡ ልጁን ፡ ያገለግ
ለው ፡ ዘንድ ፡ ለእርሱ ፡ ይገባል ። ለእርሱና ፡
ለልጆቹ ፡ ባሉበት ፡ ዘመን ፡ ልክ ፡ ያገለግሉት ፡
ዘንድ ፡ በእርሱ ፡ ላይና ፡ በልጆቹ ፡ ላይ ፡ ሊጠ

፩ሺ.፶ ወማዕሠንስ ፡ ትትፈጸም ፡ በአማህያኒሁ ፡ ውስተ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አው ፡ በሀልዎቱ ፡ ለሊቀ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አው ፡ ቀሲስ ፡ አው ፡ በ፫ቱ ፡ ሰማዕታት ፡ ወትኩን ፡ በመልእክቱ ፡ አው ፡ በጽሒፈ ፡ ትእዛዙ ። ወእመሰ ፡ ኮነ ፡ በትእዛዙ ፡ ይከውን ፡ ፍትሑ ፡ ዘእሁ ፡ ከመ ፡ ፍትሐ ፡ ተዋርሶ ፡ ወማዕሠንስ ፡ ይከውን ፡ ለኵሉ ፡ አግብርት፡ አው ፡ በፍልጠት ።

፩ሺ.፶፩ ወዘአጥረየ ፡ ፫ተ ፡ አግብርተ ፡ ወአግዓዘ ፡ ፩ደ፡ ይደልዎ ፡ ሎቱ ፡ ወለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ይሚጥ ፡ እለ ፡ ተርፉ ፡ ይደልዎ ።

፩ሺ.፶፪ ወዓዲ ፡ ማዕሠን ፡ ትከውን ፡ ለአማዕዝ ፡ ገብር ፡ ኵለንታሁ ፡ ወለክፍል ፡ እምኔሁ ፡ ወዘሰ ፡ መለከ ፡ ማልስተ ፡ እደ ፡ እምን ፡ ገብሩ ፡ ወአግዓዞ ፡ ብዉሕ ፡ ሎቱ ። ወለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ሠይጦ ፡ ኵለንታሁ ፡ ወአማዕዞተ፡ ይደሉ ፡ ላዕለ ፡ ተሳትፎቱ ፡ በሤጠ ፡ ዘእሁ ፡ በዘኮነ ፡ ወእምከመ ፡ ተማየጠ ፡ እምኔሆሙ ፡ ይደልዎ ፡ አግዕዞቱ ፡ ወሤጠ ፡ ትንድ ፡ እምሳለ ፡ ንዋይ ፡ በጊዜ ፡ ንቡር ፡ ወተባዝኖ ፡ ወሕጸጸ ፡ ወፍድፋዴ ፡ በእምባነ ፡ ግብረ ፡ እዴ ፡ ወሐጸጼ ፡ ወኢያእምሮቱ ፡ አው ፡ ብዙኀ ፡ ዓመታቲሁ ። ወይደሉ ፡ ተማይጦ ፡ ምእመን ፡ እም እለ ፡ ኢኮኑ ፡ ምእመናነ ፡ በዘይደልዎ ፡

፩ሺ.፶፫ ወይማዕዝ ፡ ገብር ፡ እምእግዚኡ ፡ በእንተ ፡ ፯ቱ ፡ ግብራት ። ቀዳማዊ ፡ ለእመ ፡ ቀነዮ ፡ ፩ዱ፡ እምወላድያኒሁ ፡ ወእምእለ ፡ ተደምሮሙ ፡ አው ፡ ለእመ ፡ ቀነዮ ፡ ፩ዱ ፡ እምውሉዶሙ ፡ ወኢለ ፡ እምደንገፈሆሙ ፡ አው ፡ ፩ዱ ፡ እምአኃዊሁ ፡ አው ፡ ፩ዱ ፡ እምእለ ፡ ይወርስዎ ፡ ይደልዎሙ ፡ አግዕዞቱ ። ወለእመ ፡ መለከ ፡ ክፍለ ፡ እምኔሁ ፡ አው ፡ ፩ ፡ ካልእ ፡ ዘይመልኮ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ውእቱ ፡ ባዕለ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይማየጥ ፡ ኵለንታሁ ፡ ወያማዕዝ ፡ ኵለንታሁ ።

፩ሺ.፶፬ ወዳግም ፡ ለእመ ፡ ተወክፈ ፡ ውእቱ ፡ አው ፡ ብእሲቱ ፡ በጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ አው ፡ ወለቱ፡ በአእምሮ ፡ ወላዲያኒሃ ፡ አው ፡ ኮነ ፡ ከሀነ ፡ በፈቃደ ፡ እግዚኡ ፡ አው ፡ ኮነ ፡ መነኮሰ ፡ ይደሉ ፡ እንከ ፡ አግዕዞቱ ።

፩ሺ.፶፭ ወሣልስ ፡ ለእመ ፡ ረሰዮ ፡ ሐራዌ ፡ ይደሉ ፡



ስን ፡ እይደለም ። የገዙት ፡ ሁሉ ፡ ለእነርሱ ፡ ይሁን ። ባርነት ፡ በዚህ ፡ ውሳኔ ፡ ትሆናለችና ።

፩ሺ.፶ ነፃነትስ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ እለቃው ፡ ኢጲስቆጶስ ፡ ወይም ፡ ቄስ ፡ ወይም ፡ ፫ ፡ ምስክሮች ፡ ባሉበት ፡ በግልጽ ፡ ትፈጸማለች ። በደብዳቤው ፡ ወይም ፡ ትእዛዙን ፡ በመጻፍ ፡ ትሁን ። በትእዛዙ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ፍርዱ ፡ እንደ ፡ መወራረስ ፡ ፍርድ ፡ ይሆናል ። ነፃነትስ ፡ ለባሪያዎች ፡ ሁሉ ፡ ወይም ፡ በመለየት ፡ ይሆናል ።

፩ሺ.፶፩ ፫ ፡ ባሮች ፡ የገዛ ፡ ሰው ፡ እንዱን ፡ ነፃ ፡ ቢያወጣው ፡ ይገባዋል ። የቀሩትንም ፡ ሊሸጥ ፡ ቢወድ ይገባዋል ።

፩ሺ.፶፪ ዳግመኛም ፡ የባሪያን ፡ ሁለመናውን ፡ ከእርሱም ፡ በክፊል ፡ ነፃ ፡ ማውጣት ፡ ትሆናለች ። ከባሪያው ፡ ሦስት ፡ እጅ ፡ የገዛ ፡ ሰው ፡ ነፃም ፡ ሊያወጣው ፡ ቢወድ ፡ መብትቱ እለው ፡ በሙሉ፡ ሊሸጠው ፡ ነፃም ፡ ሊያወጣው ፡ ቢወድ ፡ በዞነው ፡ በዋጋው ፡ ሊስማማ ፡ ይገባል ። ከእነርሱም ፡ ቢገዛ ፡ ነፃ ፡ ሊያወጣው ፡ ይገባዋል ። የተገዢውም ፡ ዋጋ ፡ በታወቀ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ገንዘብነቱ ፡ ነው ። ሊበዛና ፡ ሊያንስ ፡ በእጁ ፡ ሥራ ፡ ልክ ፡ መብዛትና ፡ ማነስ ፡ እንዳለማወቁ ፡ ወይም ፡ እንደዕድሜው ፡ መብዛት ፡ ነው ። አማኒውን ፡ (ባሪያ) ፡ ካላመኑት ፡ ሰዎች፡ በሚገባው ፡ መግዛት ፡ ይገባል ።

፩ሺ.፶፫ ባሪያ ፡ ከጌታው ፡ ስለ ፡ ፯ ፡ ሥራዎች ፡ ነፃ ፡ ይውጣ ። መ፩መሪያው ፡ ከወላጆቹ ፡ ከቀደሚቻውም ፡ (ካያቶቹ) ፡ አንዱ ፡ ቢገዛው ፡ ወይም ፡ ከልጆቻቸውና ፡ ከእነርሱም ፡ ቀጥሎ ፡ ካሉት ፡ (ከልጅ ፡ ልጆቻቸው) ፡ እንዱ ፡ ቢገዛው ፡ ወይም ፡ ከወንድሞቹ ፡ አንዱ ፡ ወይም ፡ ከወራሾቹ ፡ ወገን ፡ እንዱ ፡ ቢገዛው ፡ ነፃ ፡ ማውጣቱ ፡ ይገባቸዋል ። ከእርሱ ፡ በከፊል ፡ ቢገዛው ፡ ወይም፡ ሌላ ፡ የሚገዛው ፡ ቢኖር ፡ እርሱ ፡ ባለጸጋ ፡ ከሆነ ፡ በሙሉ ፡ ገዝቶ ፡ በሙሉ ፡ ነፃ ፡ ሊያወጣው ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ.፶፬ ሁለተኛው ፡ እርሱ ፡ ወይም ፡ ሚስቱ ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ልጁ ፡ ወላጆቿ ፡ እውቀው ፡ በጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ ቢቀበሉት ፡ ወይም ፡ በጌታው ፡ ፈቃድ ፡ ካህን ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ መነኮስ ፡ ቢሆን ፡ ነፃ ፡ ማውጣቱ ፡ ይገባል ።

፩ሺ.፶፭ ሦስተኛው ፡ ወታደር ፡ ቢያደርገው ፡ ነፃ ፡ ማው

እግዕዞቱ ።

፩ሺ፶፮ ወራብዕሂ ፡ ሰእመ ፡ አድኀኖ ፡ ለእግዚኡ ፡ እምቀትል ፡ እመሂ ፡ በተቀትሎቱ ፡ ዘዮንቱሁ ፡ አው ፡ እምክር ፡ ከመ ፡ ይትዐቀብ ፡ ያግዕዞ ፡ በፍዳሁ ።

፩ሺ፶፯ ወኃምስሂ ፡ ለእመ ፡ እግዐዘዋ ፡ ለዕንስት ፡ ወልዳኒ ፡ ግዑዝ ፡ ውእቱ ።

፩ሺ፶፰ ወሳድስሂ ፡ ለእመ ፡ ተአሰረ ፡ ገብር ፡ ወተመይጠ ፡ ኀበ ፡ እግዚኡ ፡ በፈቃዱ ፡ እምድኅረ ፡ ጸንዐ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ ጸላኢ ፡ ይደልዎ ፡ ግዕዛን ።

፩ሺ፶፱ ወሳብዕሂ ፡ ለእመ ፡ ሞተ ፡ እግዚኡ ፡ ወአልቦ ፡ ዘይወርስ ፡ ዘእንበለ ፡ እግዝእቱ ፡ ወቤተ ፡ መንግሥት ፡ ይደልዎ ፡ ግዕዛን ።

፩ሺ፷ ወዘእግዐዘ ፡ ገብሮ ፡ በእንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አው ፡ በእንተ ፡ እይኒ ፡ ገጽ ፡ እምገጸት ፡ እመ ፡ ኮነ ፡ ፍቁረ ፡ እው ፡ ጽሉእ ፡ ይደልዎ ፡ ግዕዛን ።

፩ሺ፷፩ ወዘሂ ፡ ተአመነ ፡ እምግዑዛን ፡ በረቀ ፡ ቅንየት ፡ ለካልኡ ፡ ወፈቀደ ፡ ከመ ፡ ይሠየጥ ፡ ወለእመ ፡ ኀለፈ ፡ መዋዕሊሁ ፡ እምኆ ፡ ዓመት ፡ ወተዓገሠ ፡ ላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ ተአምኖ ፡ እስከ ፡ ይሠይጦ ፡ አው ፡ ይሬስዮ ፡ ሕጹ ፡ ሰብእሲቱ ፡ ይከውን ፡ ገብረ ። ወፈድፋደሰ ፡ ሶበ ፡ ተነግረ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ተሰነአወ ፡ ምስለ ፡ ዘኀሠጦ ፡ ላዕለ ፡ ሤጠ ፡ ዚአሁ ። ወእመሰ ፡ ኢበጽሐ ፡ ኀበ ፡ ዝንቱ ፡ ዓመታት ፡ ድልው ፡ ለፈታሒ ፡ ወለመኰንን ፡ ከመ ፡ ያውዕእዎ ፡ እምእደዊሁ ፡ ወእምእደ ፡ ዘተሣየጠ ፡ እምኔሁ ፡ ወይኩን ፡ ግዑዘ ።

፩ሺ፷፪ ወይደሉ ፡ ለገብር ፡ ዘእግዓዝዎ ፡ ከመ ፡ ይትመየጥ ፡ ውስተ ፡ ቅንየቱ ፡ ሶበ ፡ ተጠየቀ ፡ ቦቱ ፡ ኀበ ፡ ፈታሒ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ረገሞ ፡ ለእግዚኡ ወዘበጦ ፡ አው ፡ ዘበጦሙ ፡ ለውሉዱ ፡ ዘእንበለ ፡ ሥምረቱ ፡ አው ፡ እኀጐለ ፡ ንዋዮ ፡ በእደ ፡ ካልአን ፡ ፈቂዶ ፡ ከመ ፡ ያሕሥም ፡ ላዕሌሁ ። ወፈድፋደሰ ፡ እመ ፡ ገብረ ፡ ሕሡመ ፡ ላዕለ ፡ ሕይወቶሙ ፡ ይደልዎ ፡ በከመ ፡ ተአዘዘ ፡ በአሪት ። ወኢይኅድጎ ፡ እግዚኡ ፡ በግዕዛኑ ፡ ወይፃእ ፡ ከዊኖ ፡ ዕሩቀ ፡ እምብዕሉ ።

፩ሺ፷፫ ወኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ትትወሰብ ፡ አግዓዚት ፡ ለገብር ፡ ወትንበር ፡ ኀቤሁ ፡ በቤተ ፡ እግዚኡ ፡ አው ፡ ታንብሮ ፡ ኀቤሃ ፡ በፈቃደ ፡ እግዚኡ ፡ ወእሜሃ ፡ ትኩውን ፡ ይእቲ ፡ ከማሁ ፡ ውስተ ፡



ጣቱ ፡ ይገባል ።

፩ሺ፶፮ አራተኛው ፡ ጌታውን ፡ ከሞት ፡ ቢያድነው ፡ ሰለእርሱ ፡ በመዋጋትም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ እንዲጠነቀቅ ፡ ቢመክረው ፡ ብድሩን ፡ (ዋጋውን) ፡ ነፃ ፡ ያውጣው ።

፩ሺ፶፯ አምስተኛውም ፡ የፀነሰችውን ፡ ባሪያ ፡ ነፃ ፡ ቢያወጧት ፡ ልጅዋም ፡ ነፃ ፡ ነው ።

፩ሺ፶፰ ስድስተኛውም ፡ ባሪያ ፡ ቢታሠር ፡ በጠላት ፡ እጅ ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፡ በፈቃዱ ፡ ወደጌታው ፡ ቢመለስ ፡ ነፃነት ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ፶፱ ሰባተኛውም ፡ ጌታው ፡ ቢሞት ፡ ከእመቤቱና ፡ ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ በቀር ፡ ወራሽ ፡ ባይኖረው ፡ ነፃነት ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ፷ ባሪያውን ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ ከምክንያቶች ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ነፃ ፡ ያወጣ ፡ ሰው ፡ የሚወደውም ፡ ወይም ፡ የሚጠላው ፡ ቢሆን ፡ ነፃነት ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ፷፩ ነፃ ፡ ከሚወጡት ፡ ባሮች ፡ በመገዛት ፡ ደብዳቤ ፡ ሰሌላው ፡ ቢያምን ፡ ሊሸጥም ፡ ቢወድ ፡ ዕድሜዉም ፡ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ ቢያልፍ ፡ እስኪሸጠው ፡ ወይም ፡ ለሚስቱ ፡ ማጫ ፡ እስኪያደርገው ፡ ድረስ ፡ በዚህ ፡ በማመኑ ፡ ቢታገሥ ፡ (ቢፀና) ፡ ባሪያ ፡ ይሆናል ። ይልቁንም ፡ ከሸጠው ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ በዋጋው ፡ እንደተስማማ ፡ በተነገረ ፡ ጊዜ ፡ ወደዚህ ፡ ዓመት ፡ (ኻያ ፡ ዘመን) ፡ ባይደርስ ፡ ግን ፡ ሰዳኛና ፡ ለገዢ ፡ ከእጁና ፡ ከእርሱ ፡ ከገዛውም ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ሊያወጡት ፡ አገባብ ፡ ነው ። ነፃም ፡ ይሁን ።

፩ሺ፷፪ ነፃ ፡ ያወጡት ፡ ባሪያ ፡ ጌታውን ፡ እንደረገመውና ፡ እንደመታው ፡ ወይም ፡ ልጆቹን ፡ ያለ ፈቃዱ ፡ እንደመታቸው ፡ ወይም ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ሊያደርግ ፡ ወድዶ ፡ በሌሎች ፡ እጅ፡ ገንዘቡ ፡ እንዲጠፋበት ፡ በዳኛ ፡ ዘንድ ፡ ቢመሰከርበት ፡ ወደመገዛቱ ፡ ሊመለስ ፡ ይገባል ። ይልቁንም ፡ በሕይወታቸው ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ቢሠራ ፡ በኦሪት ፡ እንደታዘዘው ፡ ይገባዋል ። ጌታው ፡ በነፃነቱ ፡ አይተወው ። ከሀብቱ ፡ ባዶ ፡ ሁኖ ፡ ይውጣ ።

፩ሺ፷፫ ነፃ ፡ የወጣች ፡ ባሪያ ፡ ሰባሪያ ፡ ሚስት ፡ ልትሆን ፡ በጌታውም ፡ ቤት ፡ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ ልትኖር ፡ ወይም ፡ በጌታው ፡ ፈቃድ ፡ በእርሱዋ ዘንድ ፡ ልታኖረው ፡ አይገባም ። ያንጊዜ ፡ እር

አንቀጽ ፡ ፴፪ ።

ግብርናት ፡ ለእግዚእ ።

፩ሺ፰፻፬ ወዘኔሰ ፡ ለገብረ ፡ ካልኡ ፡ ዘኢኮነ ፡ ሎቱ ፡ ወኀብአ ፡ ወአርኀቆ ፡ ይደሉ ፡ ላዕሌሁ ፡ መይጦቶ ፡ ገብር ፡ ለእግዚኡ ፡ ወይወስክ ፡ ላዕሌሁ ፡ ካልአ ፡ ገብረ ፡ እው ፡ ሤጦ ። ወከማሁ ፡ ዘአኀደረ ፡ ገብረ ፡ ካልኡ ፡ ዘኢኮነ ፡ ሎቱ ፡ ወረሰዮ ፡ ገብረ ፡ ለርእሱ ፡ እንዘ ፡ የአምር ፡ ከመ ፡ ውእቱ፡ ኮነ ፡ ገብረ ፡ ካልኡ ፡ ውእቱ ፡ እሜሃ ፡ ይኩን ፡ ከማሁ ፡ በውስተ ፡ ግብርናት ፡ ለዘ ፡ በእማን ፡ እግዚአ ፡ ዚአሁ ።

ስለ ፡ ሞግዚትነት ።

ቧም ፡ እንደእርሱ ፡ ለጌታው ፡ በተገዥነት ፡ ውስጥ ፡ ትሆናለች ።

፩ሺ፰፻፬ የእርሱ ፡ ያልሆነውን ፡ የሌላውን ፡ ባሪያ ፡ ያባበለ ፡ እርቆም ፡ የሸሸገ ፡ ሌላ ፡ ሁለተኛ ፡ ባሪያ ፡ ወይም ፡ ዋጋውን ፡ ጨምሮ ፡ ለጌታው ፡ ሊመልስው ፡ ይገባል ። እንደዚኹውም ፡ የእርሱ ፡ ያልሆነውን የሌላውን ፡ ባሪያ ፡ ያሳደረ ፡ የሌላው ፡ ባሪያ ፡ እንደሆነም ፡ እያወቀ ፡ ለራሱ ፡ ባሪያ ፡ ያደረገው ፡ ያንጊዜ ፡ እርሱ ፡ ለዕውነተኛው ፡ ጌታው ፡ በባርነት ፡ እንደእርሱ ፡ ይሁን ።

---

## አንቀጽ ፡ ፴ወ፫ ።

በእንተ ፡ ምግብና ።

፩ሺ፰፻፭ ዘእምጽእዎ ፡ እምአብጥሊስ ፡ ወዘይመስሎ ፡ ወዘይደሉስ ፡ ለምግብና ፡ ፪ቱ ፡ ግብራት ። ቀዳማዊ ፡ ለዘኢይትነሠሎ ፡ ያእምር ፡ ዘውስተ ፡ ልቡ ፡ ዘይደሉ ፡ ለፍጻሜ ፡ ጠባይዕ ፡ ወዘይሜኒ፡ ለሥምረቱ ፡ እመኒ ፡ በምክንያተ ፡ ኃኔን ፡ ዘያጌብሮ ፡ ወዝንቱ ፡ ዐብድ ፡ ውእቱ ። አው ፡ በአማስኖ ፡ ናላሁ ፡ በደዌ ፡ ወዝንቱኒ ፡ ዝንጉዕ፡ ውእቱ ፡ ዘተደመት ፡ ግብሩ ፡ አው ፡ ሶበ ፡ ኢበጽሐ ፡ ናላሁ ፡ ፍጹመ ፡ ወዝንቱኒ ፡ ሕፃን ፡ ውእቱ ፡ ዘኢበጽሐ ፡ እስከ ፡ ፲ወ፰ቱ ፡ ዓመት ። አው ፡ እስመ ፡ ቀዳሚት ፡ ግብሩ ፡ ለእመ ፡ ደከመት ፡ በጠባይዕ ፡ እንዘ ፡ ይትጌበር ፡ ባቲ ፡ ወውእቱ ፡ ድኅረ ፡ ልህቀ ፡ ወቀርበ ፡ ኀበ ፡ ፺ቱ ዓመት ፡ ወቀዳሚት ፡ ግብሩ ፡ ኮነት ፡ ድኅንተ ፡ ወፍጽምተ ፡ ወባሕቱ ፡ ኢተገበረ ፡ ባቲ ፡ በዘይደልዋ ፡ ወውእቱ ፡ ስኡን ። አው ፡ እመ ፡ ውእቱ ፡ ተገበረ ፡ ባቲ ፡ ግብረ ፡ በዘያሐሥም ፡ በዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ወያኀሪታ ፡ ወዝንቱኒ ፡ እንዝህሉል ፡ ውእቱ ፡ በሥርዓቱ ፡ ወንዋዩ ፡ ዘከመ ፡ ዘራዊ ፡ በእስተዋፅኦታት ፡ ወአጥፍአ ። ወዝንቱኒ ፡ ይትዓቀብ ፡ በጽኑዕ ፡ ከመ ፡ ካዕበ ፡ እንዝኀሉለ ፡ ኢይኩን ፡ በውስተ ፡ ሃይማኖቱ ፡ በሰቢስ ፡ ሕርመታት ፡ ወአብዝኆ ፡ ፍትወታት ፡ ወዜናሁስ ፡ ለእንዝኀሉል ፡ ይትናጸር ፡ ምስለ ፡ ዜናሁ ፡ ለልብው ።

## አንቀጽ ፡ ፴፫ ።

ስለ ፡ አስተዳደር ፡ ይናገራል ።

፩ሺ፰፻፭ ከአብጥሊስና፡ከሚመስለውም፡የመጡት፡ነው። ለአስተዳደር፡የሚገቡስ፡፪፡ሥራዎች፡ናቸው ። መጀመሪያው ፡ ለፍጹም፡ባሕርዩ፡የሚገባውንና ለፈቃዱ፡የሚስማማውን፡በልቡ፡ውስጥ ፡ ያለውን፡ሊያውቅ፡ለማይቻለው፡ሰው ፡ ነው። በሚጥለው፡ኃኔን፡ምክንያትም፡ቢሆን ፡ ይህም፡ዐላዋቂ፡ነው። ወይም፡በደዌ ፡ አእምሮውን፡በማጣት፡ይኸውም፡የቀደመች፡ሥራውን ፡ የሚዘነጋ፡ነው። ወይም፡አእምሮው፡ወደፍጹምነት ፡ ያልደረሰ፡ይኸውም ፡ እስከ ፡ አሥራስምንት ፡ ዓመት፡ያልደረሰ፡ሕፃን፡ነው። ወይም፡የመጀመሪያዪቱ፡ሥራው፡እየሠራበት፡በባሕርይ ፡ ብትደክም፡ይኸውም፡ሸምግሎ፡ወደመቶ፡ዓመት ፡ ስለቀረበ፡ነው። የቀደመች፡ግብሩም፡ደኅና፡ፍጽምት፡ነበረች። ነገር፡ግን፡በሚገባት ፡ አልሠራባትም። ይኸውም፡ደካማ፡ነው። ወይም ፡ በዚህና፡በኋለኛው፡ዓለም፡የሚጎዳ ፡ ሥራ፡ቢሠራባት፡ይኸውም ፡ በሥርዓቱና ፡ (በአስተዳደሩ ፡) በገንዘቡ ፡ ንዝኅላል ፡ ነው ። ይኸውም ፡ በማወጣጣትና ፡ በማጥፋት ፡ ገንዘቡን ፡ እንደሚበትን ፡ ነው ። ይህም ፡ የተከለከለውን ፡ በመልበስና ፡ ዝሙትን ፡ በማብዛት ፡ ዳግመኛ ፡ በሃይማኖት ፡ ንዝኅላል ፡ እንዳይሆን ፡ በጽኑ ፡ ይጠበቅ ። የንዝኅላል ፡ ሰው ፡ አስተያየት ፡ ከአስተዋይ ፡ ሰው ፡ አስተያየት ፡ ጋራ ፡ ይነፃፀራል ።

አንቀጽ ፡ ፴፪ ።

፩ሺ፰፻፯ ወግብርኒ ፡ ዳግማዊ ፡ ዘይከልእ ፡ ለለባዊ ፡ መግቦተ ፡ ርእሱ ፡ በንዋዩ ፡ ወውእቱ ፡ ግብር ። ወለዘሂ ፡ ሀለወ ፡ በታሕተ ፡ ምግብና ፡ እመ ፡ ኮነ ፡ ዐብደ ፡ አው ፡ ዝንጉዐ ፡ አው ፡ ሕፃን ፡ ንኡስ ፡ አው ፡ አረጋዊ ፡ ዘረስዐ ፡ በመዋዕሊሁ ። ኢይደልዎሙ ፡ ለእሉ ፡ ከመ ፡ ይሥርዑ ፡ ኢ ፡ በአስተዋስዖ ፡ ወኢ ፡ በተአምኖ ፡ ቃል ፡ ኢ ፡ ለንፍሶሙ ፡ ወኢ ፡ ለካልአኒሆሙ ። ወእመኒ ፡ ኮነ ፡ የዋሀ ፡ አው ፡ እንዝኅሉለ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይትመገብ ፡ በንዋየ ፡ ርእሱ ፡ ወአኮ ፡ ንዋየ ፡ ካልኡ ፡ በትእዛዘ ፡ አመጋቢሁ ፡ ባሕቲቱ ።

፩ሺ፰፻፰ ወለእመኒ ፡ ገብር ፡ ውእቱ ፡ ይደሉ ፡ መግቦቱ ፡ በትእዛዘ ፡ እግዚኡ ፡ ባሕቲቱ ፡ ወይደልዎ ፡ እምድኅረ ፡ ግዕዛን ፡ ከመ ፡ ይእመን ፡ ሳሰለ ፡ ነፍሱ ፡ በከዊነ ፡ ግብርናት ። ወለእሉ ፡ ሰበ ፡ አጥፍኡ ፡ ምንተኒ ፡ እምንዋዮሙ ፡ ይደልዎሙ ፡ ይፍድዩ ። ወለእመ ፡ አበዘ ፡ ዘሀሎ ፡ ታሕተ ፡ ምግብና ፡ በደዌሁ ፡ ትእዛዘ ፡ ሠናየ ፡ ሕጋዊተ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዐብደ ፡ አው ፡ ዝንጉዐ ፡ ኮነት ፡ አማን ፡ ትእዛዞሙ ፡ እምድኅረ ፡ ሞቶሙ ። ወለእመኒ ፡ ኮኑ ፡ ካልአኒሆሙ ፡ ኢይከውን ፡ አማን ፡ እምኔሃ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘይፌጽሞ ፡ መኰንን ፡ ወፈታሒ ።

፩ሺ፰፻፱ ወመጋቢኒ ፡ ውእቱ ፡ አብ ፡ ለእመ ፡ ኢሀለወ ፡ ታሕተ ፡ ምግብና ፡ ወእምዝ ፡ ዘይሜግብ ፡ አብ ፡ ወእምዝ ፡ እኁ ፡ በቢጾ ፡ ወእምዝ ፡ እምኔሁ ፡ ወእምዝ ፡ እኅወ ፡ አብ ፡ ወእምዝ ፡ ወልደ ፡ እኅወ ፡ አብ ፡ ወዘይከውን ፡ ለባዊ ፡ እምእል ፡ ከተ ፡ ኵሎሙ ፡ ይቀድም ፡ እምካልኡ ። ወዘማሰነ ፡ ልቡ ፡ ወሎቱ ፡ ወልድ ፡ ኅሩይ ፡ ውእቱ ፡ ድልው ፡ እምዝኩራን ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ምግብና ፡ በላዕሌሁ ። ወእምድኅረ ፡ እሉ ፡ ኵሎሙ ፡ አብ ፡ በንብረት ፡ ዘውእቱ ፡ ሐፃኒ ፡ ወለእመ ፡ ኢተረክበ ፡ ፩ዱኒ ፡ እምእለ ፡ ተዘከሩ ፡ ፈታሒ ፡ ይሢም ፡ መጋቤ ፡ ምእመነ ፡ ዘይበቍዕ ፡ ወይሬእዩ ፡ ኪያሁ ።

፩ሺ፰፻፲ ወኢይደልዎ ፡ ለዘተሠይመ ፡ መጋቤ ፡ ከመ ፡ ይሢጥ ፡ ምንተኒ ፡ ንዋየ ፡ ዘእንበለ ፡ ሥዩም ፡ ዘእምታሕቴሁ ፡ ወዘእንበለ ፡ በአምጣነ ፡ ሤጡ

ስለ ፡ ሞግዚትነት ።

፩ሺ፰፻፯ ሁለተኛው ፡ ግብር ፡ ዐዋቂን ፡ በገንዘቡ ፡ ራሱን ፡ ከማስተዳደር ፡ የሚከለክለው ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ባሪያ ፡ ነው ። በመተዳደር ፡ ስር ፡ ያለ ፡ ዐላዋቂ ፡ ወይም ፡ ዝንጉዕ ፡ ወይም ፡ ትንሽ ፡ ሕፃን ፡ ወይም ፡ በዘመኑ ፡ ያረጀ ፡ ሽማግሌ ፡ ቢሆን ፡ ለእነዚህ ፡ በማጋባት ፡ ለራሳቸውም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ለሌሎቹ ፡ በቃል ፡ መተማመን ሊሠሩ ፡ አይገባቸውም ። አላዋቂ ፡ ወይም ፡ ንዝኅላል ፡ ቢሆን ፡ በሌላው ፡ ገንዘብ ፡ ያይደለ ፡ በራሱ ፡ ገንዘብ ፡ በአስተዳዳሪው ፡ ትእዛዝ ፡ ብቻ ፡ ሊተዳደር ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ፰፻፰ ባሪያ ፡ ቢሆንም ፡ በጌታው ፡ ትእዛዝ ፡ ብቻ ፡ ሊተዳደር ፡ ይገባዋል ። ከነፃነትም ፡ በኋላ ፡ በባርነት ፡ ሁኔታ ፡ በራሱ ፡ ሊያምን ፡ ይገባዋል ። እሊህም ፡ ከገንዘባቸው ፡ አንዳች ፡ ቢያጠፉ ፡ ሊከፍሉ ፡ ይገባቸዋል ። በመተዳደር ፡ ስር ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ በደዌው ፡ ጊዜ ፡ ሕጋዊ ፡ የሆነ ፡ መልካም ፡ ትእዛዝ ፡ ቢያዝ ፡ አላዋቂ ፡ ዝንጉዕ ፡ ቢሆንም ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ትእዛዛቸው ፡ የታመነች ፡ ሆነች ። እንደነርሱም ፡ ያሉ ፡ ቢሆኑ ፡ ገኘርና ፡ ዳኛ ፡ ከሚፈጽመው ፡ በቀር ፡ ከእርሷ ፡ የተነሣ ፡ እውነተኛ ፡ አትሆንም ።

፩ሺ፰፻፱ አባትም ፡ በመተዳደር ፡ ስር ፡ ካልኖረ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ነው ። ቀጥሎም ፡ የሚያስተዳድር ፡ አባት ፡ ከዚያም ፡ ቀጥሎ ፡ ታላቅ ፡ ወንድም ፡ ከዚያም ፡ ቀጥሎ ፡ አያት ፡ ከዚያም ፡ ቀጥሎ ፡ ያባት ፡ ወንድም ፡ (አጎት) ፡ ከዚያም ፡ ቀጥሎ ፡ የአባት ፡ የወንድም ፡ ልጅ ፡ (ያጎት ፡ ልጅ ፡ ነው ። ከእነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ዐዋቂ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ከሌላው ፡ ይቀድማል ። አእምሮው ፡ የጠፋ ፡ ሰው ፡ የተመረጠ ፡ ልጅ ፡ ቢኖረው ፡ ከተነገሩት ፡ ሰዎች ፡ ይልቅ ፡ አስተዳደር ፡ ለእርሱ ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ። ከእነዚህ ፡ ሁሉ ፡ በኋላ ፡ በንብረት ፡ ላይ ፡ የሚያዝ ፡ አባት ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ሞግዚት ፡ ነው ። ከተነገሩት ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡ እንኳ ፡ ባይገኝ ፡ ዳኛ ፡ የሚጠቅም ፡ የታመነ ፡ ሰው ፡ ይሹም ። እርሱንም ፡ ይጠብቅ ፡ (ይቆጣጠር) ።

፩ሺ፰፻፲ አስተዳዳሪ ፡ ሆኖ ፡ ለተሾመ ፡ ሰው ፡ ከበታቹ ፡ ከተሾመው ፡ ጋር ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ባስቀመጠበት ፡ ጊዜ ፡ በነበረው ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፡ ካልሆነ ፡

አንቀጽ ፡ ፴፱ ።

በጊዜ ፡ እንበረ ፡ ወኢከመ ፡ ይድፍር ፡ በንዋዩ ፡ በነጊድ ፡ እው ፡ በሠይጥ ፡ በዕድሜ ፡ ዘእንበለ ፡ በእኂዞተ ፡ ክሡተ ፡ ወበዋሕስ ። ወኢይለቅሕ ፡ ምንተኒ ፡ እምኔሁ ፡ እላ ፡ ለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ነጊደ ፡ ወጽሕቀ ፡ ይደልዎ ፡ በግብር ፡ ከመ ፡ ያንብሮ ፡ ማኅፀንተ ፡ እስመ ፡ ልቃሕ ፡ ለባዕል ፡ በትሕቢት ፡ እው ፡ በእኅዝ ፡ ይኄይስ ፡ እምእ ማኅፅኖት ፡ ለእመ ፡ ተሰነእዉ ፡ ተለቃሒ ፡ ወተ ማኅፃኒ ፡ ኅቤሁ ። ማኅፀንትሰ ፡ በእንተ ፡ ተእ ምኖቱ ፡ ወተዓቅቦቱ ፡ ለዘይሁብዎ ፡ እስመ ፡ ለተለቃሒ ፡ ቦቱ ፡ ተሐባዪ ፡ በኵሉ ፡ ግብር ፡ ወዘአዕቀብዎሰ ፡ ማኅፀንተ ፡ አኮ ፡ ከማሁ ።

፩ሺ.፸ ወለእመ ፡ ተናፈቀ ፡ ዘሀሎ ፡ ታሕተ ፡ ምግብና ፡ ምስለ ፡ መጋቢሁ ፡ ይኩን ፡ በከመ ፡ ቃሉ ፡ ለዘእ መገብዎ ፡ ዘእንበለ ፡ ዳእሙ ፡ ለእመ ፡ አም ጽእ ፡ ስምዐ ፡ ጥዩቀ ። ወለእመ ፡ ነገረ ፡ ዘእመ ገብዎ ፡ ወይቤ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ አስተዋፅአ ፡ ንዋዮ ፡ ላዕሌሁ ፡ እው ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ጠፍእ ፡ በእዴሁ ፡ ዘእንበለ ፡ ተዓውሮ ፡ ቃልኒ ፡ ቃለ ፡ ዚእሁ ። ወለእመ ፡ ይቤ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ወሀቦ፡ ሎቱ ፡ እምድኅረ ፡ ፀአተ ፡ እምሕፅኑ ፡ ኢይትወ ከፉ ፡ ቃሎ ፡ ዘእንበለ ፡ በስምዐ ፡ ጥዩቀ ።

፩ሺ.፸፩ ወይደልዎ ፡ ለዘእመገብዎ ፡ ከመ ፡ ያስተዋ ፅእ ፡ ለዘሀሎ ፡ ታሕተ ፡ ምግብናሁ ፡ በከመ ፡ ሥርዓቶሙ ፡ ለእለ ፡ ነበሩ ፡ ከማሁ ፡ ወበሐሳበ ፡ ንዋዩ ፡ ወኢያኅጥእ ፡ ምንተኒ ፡ እምግብረ ፡ መፍቅዳት ፡ በሕይወቱ ፡ ወዛቲ ፡ ይእቲ ፡ሲሳይ ወዓራዝ ፡ ወማኅደር ፡ ወእስተዋስኦ ፡ እምከመ፡ በጽሐ ፡ ጊዜሁ ፡ ወተምህሮ ፡ ግብረ ፡ እድ ፡ ዘተ ቀንዮ ፡ ወዘእእምሮ ። ወከማሁ ፡ ያስተዋፅእ ፡ ዘይትከሀሎ ፡ ላዕሌሁ ፡ ለዘሀሎ ፡ ታሕተ ፡ ምግዙ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘይጼነስ ፡ በከመ ፡ ወልዱ፡ ወውሉደ ፡ ውሉዱ ፡ ወብእሲቱ ፡ ወአኃዊሁ ፡ ወእግብርቲሁ ።

፩ሺ.፸፪ ወይደሉ ፡ ከመ ፡ ያመግብ ፡ መኑኑ ፡ ላዕለ ፡ ዘላዕሌሁ ፡ ልቃሕ ፡ ወኢይትከሀሎ ፡ ከመ ፡ ያስ ተዋፅእ ፡ በንዋዩ ፡ ዘሀሎ ፡ ወከሡትስ ፡ ዕድሜ ፡ ለዘሀሎ ፡ ታሕተ ፡ ምግብ ፡ ዘእንበለ ፡ በምግባ ራት ፡ ዘመፍቅደ ፡ ሕይወት ፡ እስከ ፡ ይፈዲ ፡ ዘተለቅሐ ። ወለእመ ፡ እምነ ፡ ዘተለቅሐ ፡ ልቃሐ ፡ ካልእ ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ ታሕተ ፡ ዝንቱ፡

ስለ ፡ ሞግዚትነት ።

እንዳች ፡ ገንዘብ ፡ ሊሸጥ ፡ አይገባውም ። በገን ዘቡም ፡ በመነገድ ፡ ወይም ፡ የታወቀ ፡ ነገር ፡ በመያዝ ፡ በዋስ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በቀጠሮ ፡ (በዱቤ) ፡ በመሸጥ ፡ ሊደፍር ፡ አይገባውም ። ከገንዘቡ ፡ ምንም ፡ አያበድር ። ወደሩቅ ፡ መሄ ድን ፡ ወድዶ ፡ ቢተጋ ፡ (ቢነግ) ፡ በግድ ፡ እደራ፡ ያኖረው ፡ ዘንድ ፡ ይገባዋል ፡ እንጂ ። ተበዳሪና ፡ ስእርሱ ፡ ዘንድ ፡ አደራ ፡ ያስቀመጡበት ፡ ከተ ስማሙ ፡ እደራ ፡ ከማስቀመጥ ፡ ይልቅ ፡ በዋስ ፡ ወይም ፡ በመያዣ ፡ ለባለጸጋ ፡ ማበደር ፡ ይሻ ላልና ። አደራስ ፡ በሚሰጡት ፡ ሰው ፡ ታማኝ ነት ፡ የሚጠበቅ ፡ ነው ። ለተበዳሪ ፡ በሥራው ፡ ሁሉ ፡ ዋስ ፡ አለውና ። አደራ ፡ ያስጠበቁት ፡ ሰው ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አይደለም ።

፩ሺ.፸ በመተዳደር ፡ ስር ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ከሹሙ ፡ ጋራ ፡ ቢጣላ ፡ የማስረጃ ፡ ምስክር ፡ ካላመጣ ፡ በቀር ፡ አስተዳዳሪ ፡ እንዳደረጉት ፡ ሰው ፡ ቃል ፡ ይሁን። አስተዳዳሪ ፡ ያደረጉት ፡ ሰው ፡ ገንዘቡን ፡ በእ ርሱ ፡ ላይ ፡ እንዳወጣጣ ፡ ወይም ፡ ያለቸልታ ፡ በእጁ ፡ እንደጠፋ ፡ ቢናገር ፡ ቃሉ ፡ ቃሉ ፡ ነው ። (እርሱ ፡ እንደተናገረው ፡ ይሁን) ። በእርሱ ፡ ስር ፡ ከመተዳደር ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ ለእርሱ ፡ ሰጠሁት ፡ ቢል ፡ ያለማስረጃ ፡ ምስክር ፡ ቃሉን ፡ አይቀበሉ ።

፩ሺ.፸፩ አስተዳዳሪ ፡ ላደረጉት ፡ ሰው ፡ በአስተዳደሩ ፡ ስር ፡ ላለው ፡ እንደርሱ ፡ ሁነው ፡ እንደሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ሥርዓትና ፡ እንደገንዘቡ ፡ ሂሣብ ፡ ሊያ ወጣጣ ፡ ይገባዋል ። ለሕይወቱ ፡ ከሚያሻው ፡ ነገር ፡ ምንምን ፡ አያሳጣው ። ይህችም ፡ ምግብ፡ ልብስ ፡ ቤት ፡ አካለ ፡ መጠንም ፡ ካደረሰ ፡ ማጋ ባት ፡ የመገዛትና ፡ የእውቀት ፡ ተግባረ ፡ እድ ፡ መማር ፡ ናት ። እንደዚኸውም ፡ ችግረኛ ፡ ቢሆ ን ፡ በአስተዳደሩ ፡ ስር ፡ ላለው ፡ የተቻለውን ፡ ያወጣጣ ፡ ይኸውም ፡ እንደ ፡ ልጁ ፡ እንደ ፡ ወንዶች ፡ ልጆቹ ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ ሚስቱ ፡ እንደወንድሞቹ ፡ እንደባሮቹ ፡ ላሉት ፡ ነው ።

፩ሺ.፸፪ ብድር ፡ ባለበት ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ዳኛ ፡ ሹም ፡ ሊሾም ፡ ይገባል ። ባለ ፡ በገንዘቡ ፡ ሊያወጣጣ ፡ አይቻለውም ። የታወቀ ፡ ቀጠሮስ ፡ ከሕይወት ፡ ፍላጎት ፡ ሥራዎች ፡ በቀር ፡ በመተዳደር ፡ ስር ፡ ላለ ፡ ሰው ፡ የተበደረውን ፡ እስኪከፍል ፡ ድረስ፡ ነው ። የተበደረ ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ በመተዳደር ፡ ስር ፡ ላለ ፡ የሌላውን ፡ ብድር ፡ ቢያምን ፡ በዚያ ፡

ምግብ ፡ ኢይከውን ፡ በውእቱ ፡ ጊዜ ፡ ወይእ ኅዞ ፡ ዕዳሁ ፡ እምድኅረ ፡ ፈድየ ፡ ልቃሕ ፡ ዘኮነ ፡ ታሕተ ፡ ምግብ ፡ በእንቲአሁ ። ወምግብኒ ፡ ይትአተት ፡ በምክንያተ ፡ አእትቶቱ ፡ ዘው እቱ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘዘሎ ፡ ታሕተ ፡ ምግብ ፡ ለባዌ ፡ ወማእምረ ፡ ወግዑዘ ፡ ያስተብቍዖ ፡ ለመኰንን ፡ ከመ ፡ ያእትት ፡ እምላዕሌሁ ፡ ሥር ዓተ ፡ አመግቦ ፡ ወሰምዐ ፡ ይኩንዎ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ይበቍዕ ፡ ለመግቦ ፡ ምግባራቲሁ ፡ ወንዋዩ ።

፪፻፸፫ ወይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ከዊነ ፡ ምግብና ፡ በዐ ቅሞ ፡ ስማዕት ፡ ከመ ፡ ይትገኀሥ ፡ እምተኰን ኖቱ ፡ ለዘአመገብዎ ፡ በላዕሌሁ ፡ ወይቅሙ ፡ ጽሒፈ ፡ ትእዛዝ ፡ በእንተ ፡ ዕድሜሁ ፡ ለምግ ብና ፡ ወከማሁ ፡ ይደሉ ፡ ዐቅሞተ ፡ ስማዕት ፡ በእንተ ፡ ተአትቶቱ ፡ ወእግበዮቱ ፡ ዝንቱ ፡ በኀበ ፡ መኰንን ፡ ከመ ፡ ይጽናዕ ፡ ተሰናእዎ ቶሙ ፡ ወይጽሐፉ ፡ ትእዛዘ ፡ ለዕድሜ ፡ አእት ቶቱ ፡ ለምግብና ።

፪፻፸፬ ወለእመ ፡ ተገአዘ ፡ ሐፃኒ ፡ ምስለ ፡ መጋቢ ፡ በእንተ ፡ ንዋይ ፡ ይፍትሖ ፡ ማእከሌሆሙ ፡ ለእመ ፡ አጥፍአ ፡ መጋቢ ፡ አው ፡ ሐፃኒ ፡ ዘእ ንበለ ፡ ዘተሴሰየ ፡ በአእምሮተ ፡ መጋቢ ፡ እመሰ ፡ ጠፍአ ፡ እንበለ ፡ እከይ ፡ አልቦ ፡ ዕዳ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወእመሰ ፡ አጥፍአ ፡ ሐፃኒ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይትዋቀስ ፡ መጋቢ ፡ አምሳነ ፡ ገብረ ። ወለእመ ፡ ከሀለ ፡ ይሴሰይ ፡ ሐፃኒ ፡ እምንዋዩ ፡ ወለእመሰ ፡ አልቦ ፡ ይሴሰይ ፡ እምንዋይ ፡ ለግ ብረ ፡ ሕይወቱ ፡ ወእስከ ፡ ይልህቅ ፡ ዘየሐፅ ንዎ ። ወዝንቱ ፡ ይደሉ ፡ ለግብረ ፡ ሲሳይ ፡ ወልብስ ፡ ወማኅደር ፡ እስከ ፡ ይበጽሕ ፡ ለኣው ስቦ ፡ ወይትሜሀር ፡ ግብረ ፡ እደ ። ወይደሉ ፡ ሎቱ ፡ ተሴስዮ ፡ ለሐፃኒ ፡ ሠናይ ፡ ሶበ ፡ ኮነ ፡ ፍጹሜ ፡ ፈቃድ ፡ በአምሳለ ፡ ወላዲሁ ፡ ወበአ ምሳለ ፡ እሙ ፡ ወአኃዊሁ ፡ ወአግብርቲሁ ፡ ዘሣ ያን ።

፪፻፸፭ ወይደልዎ ፡ ለሐፃኒ ፡ ሠናይ ፡ ይኩን ፡ ጠቢበ ፡ ወየአኀዝ ፡ ንዋዮ ፡ ወባሕቱ ፡ እኂዝሰ ፡ ወምግ ብና ፡ ኢይደልዎ ፡ ዘእንበለ ፡ መጋቢ ፡ ዘተሠ ይመ ፡ በዘተሀውከ ፡ ንዋይ ። ወሐፃኒስ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ የአኀዝ ፡ እምድኅረ ፡ ልሀቀ ፡ ዘየሐፅንዎ ፡ ወአጥረየ ፡ ንዋየ ፡ ካልአ ፡ ወከ ሠተ ፡ በአምሳነ ፡ ሕይወቱ ፡ ለሐፃኒ ፡ ኢይግ



ጊዜ ፡ አይሆንም ። ስለእርሱ ፡ ቍጥጥር ፡ የተደረ ገበትን ፡ ዕዳ ፡ ከከፈለ ፡ በኋላ ፡ ዕዳ ፡ ይይዘዋል ። ሹመት ፡ ሊያስወግደው ፡ በሚያበቃ ፡ ምክን ያት ፡ ይሻራል ። ይኸውም ፡ በመተዳደር ፡ ስር ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ አስተዋይ ፡ ዐዋቂ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ቢሆን ፡ ያስተዳደሩን ፡ ሥርዓት ፡ ከእርሱ ላይ ፡ ያርቅ ፡ ዘንድ ፡ ዳኛውን ፡ ይማልደው ። ሥራውንና ፡ ገንዘቡን ፡ ለማስተዳደር ፡ እንደ ሚበቃ ፡ ምስክር ፡ ይሁኑት ።

፪፻፸፫ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ከሾሙበት ፡ ሰው ፡ መገዛት ፡ ይርቅ ፡ ዘንድ ። ያስተዳዳሪነት ፡ ሁኔታ ፡ ምስ ክር ፡ በመጥራት ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ። ስለአስተ ዳደሩ ፡ ጊዜ ፡ ትእዛዝ ፡ በመጻፍ ፡ ይወሰኑ ። እን ደዚሁም ፡ ስለመሻሩ ፡ (መቅረቱ) ፡ ምስክር ፡ መጥራት ፡ ይገባል ። ስምምነታቸውም ፡ ይጸና ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ በዳኛ ፡ ዘንድ ፡ መግለጽ ፡ ነው ። አስተዳደሩም ፡ ለሚቀርበት ፡ ጊዜ ፡ ትእ ዛዝ ፡ ይጻፉ ።

፪፻፸፬ ሞግዚት ፡ ከመጋቢ ፡ ጋራ ፡ ስለገንዘብ ፡ ቢጣላ ፡ መጋቢ ፡ ወይም ፡ ሞግዚት ፡ አጥፍቶ ፡ እንደ ሆነ ፡ መጋቢው ፡ ዐውቆት ፡ ከተበላው ፡ በቀር ፡ በመካከላቸው ፡ ይፍረዱ ። ያለ ፡ ክፋት ፡ ቢጠፋ ፡ ግን ፡ ዕዳ ፡ የለበትም ። ሞግዚት ፡ ቢያ ጠፋ ፡ በሠራው ፡ ልክ ፡ መጋቢ ፡ ሊከራከር ፡ ይገባል ። ሞግዚት ፡ ቢችል ፡ ከገንዘቡ ፡ ይመ ገብ ፡ ባይኖረው ፡ ግን ፡ የሚያሳድጉት ፡ ሕፃን ፡ እስኪያድግ ፡ ድረስ ፡ ለቁመተ ፡ ሥጋ ፡ ያህል ፡ ከገንዘቡ ፡ ይመገብ ። ይህም ፡ ለማግባት ፡ እስኪ ደርስ ፡ ተግባረ ፡ እድንም ፡ እስኪማር ፡ ድረስ ፡ ለምግብ ፡ ሥራ ፡ ለልብስ ፡ ለቤት ፡ ሊሆን ፡ ይገ ባል ። ለመልካም ፡ ሞግዚት ፡ በአባቱና ፡ በናቱ፡ በወንድሞቹና ፡ በደጋጎች ፡ ባሮች ፡ አምሳል ፡ ፈቃድ ፡ ፈጻሚ ፡ ከሆነ ፡ መመገብ ፡ ይገባዋል ።

፪፻፸፭ ለደግ ፡ ሞግዚት ፡ ብልህ ፡ ሊሆን ፡ ገንዘቡንም ፡ ሊይዝ ፡ ይገባዋል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ቢታወቀው ፡ ገንዘብ ፡ ከተሾመው ፡ መጋቢ ፡ በቀር ፡ መያዝ ፡ ማስተዳደር ፡ አይገባውም ። ሞግዚት ፡ ግን ፡ በሕይወት ፡ ሳለ ፡ የሚያሳድጉት ፡ ልጅ ፡ እስከ ፡ አደገ ፡ የታወቀ ፡ ሌላ ፡ ገንዘብም ፡ እስከ ፡ አገኘ ፡ ድረስ ፡ ሊይዝ ፡ ይገባዋል ። ለቁመተ ፡ ሥጋው ፡

በር ፡ ምንተኒ ፡ ዘእንበለ ፡ ግብር ፡ መፍትሕዊት ፡ ዘተአክል ፡ ለሕይወት ፡ ወኢይሰትሕ ፡ ንዋየ ፡ መጋቢ ፡ ዘእንበለ ፡ በአእምሮ ፡ ሐፃኒ ፡ ወለ እመኒ ፡ ለትሉ ፡ ፩ዘመ ፡ ይትፌደዩ ፡ በጊዜ ፡ ዘይደሉ ፡ ወኢያትንደዩ ፡ እስከ ፡ ያበጽሕ ፡ ዓቅመ ፡ ወአእምሮ ፡ ዘየሐሰንዎ ።

፩ሺ.፸፯ ወኢይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይኅሥሥ ፡ ፍትሐ ፡ ለእመ ፡ ኢዘለ ፡ መጋቢ ፡ ዘይከውን ፡ ስምዐ ፡ ሎቱ ፡ በኩሉ ፡ ንዋዩ ፡ ዘአመተብዎ ፡ በቅድመ ፡ ሐፃኒ ፡ በከመ ፡ ተአገዘ ፡ ትእዛዘ ፡ በኩሉ ፡ መዋዕለ ፡ ሕይወቱ ፡ ለሐፃኒ ። ወከማሁ ፡ ይደሉ ፡ አቅሞተ ፡ ሰማዕት ፡ በእንተ ፡ አእትቶቱ ፡ ወእግ ሀይተ ፡ ዝንቱ ፡ ኀበ ፡ ፈታሒ ፡ ከመ ፡ ይጸናዕ ፡ ግብሩ ፡ ወትትሩን ፡ ትእዛዘ ፡ በኩሉ ፡ ለሐፃኒ ፡ እንበለ ፡ ይኅልፍ ፡ ሕይወቱ ።

፩ሺ.፸፰ ኀበረ ፡ ውስተ ፡ ቀኖናተ ፡ ነገሥት ፡ ወይሬልው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ላዕለ ፡ ክርስቲያን ፡ ከመ ፡ ያሁንዩ ፡ ለወላድያን ፡ ወእምኒዮን ፡ ወአኃው ፡ አበው ፡ ወአኃት ፡ ወአኃው ፡ እማት ፡ ወአኃት ፡ እማት ፡ ወኩሉ ፡ ዘተመከረ ፡ እምኔሆሙ ፡ በደዌ ፡ ለው ፡ በሕጸተ ፡ ልብ ፡ አው ፡ ረከቦ ፡ ሕርትምና ፡ ለይቁሙ ፡ በግብራቲሆሙ ፡ ዘየዐቢ ፡ እምኔሃ ፡ ወይንእስ ። ወከማሁ ፡ እንስቲያሆሙ ፡ ወእግብርቲሆሙ ፡ ወአዕርክቲሆሙ ፡ ድልወት ፡ ሎሙ ፡ አዕርዮቶሙ ። ወዝንቱ ድልው ፡ ከመ ፡ ቃለ ፡ ሐዋርያ ፡ ዘይቤ ፡ ወዘ ቦቱ ፡ አዝማድ ፡ ወኢይሔሊ ፡ በእንተ ፡ ዘይሚ ንዮሙ ፡ ወዝንቱ ፡ ክሕደ ፡ ሃይማኖቱ ፡ ወው እቱ ፡ የአኪ ፡ እምኢአማኒ ፡ ኢየአምን ።

ያሀል ፡ ከምትበቃው ፡ ሥራ ፡ በቀር ፡ እንዳች ፡ አያደርግ ። ሐፃኒ ፡ ሳያውቅ ፡ መጋቢ ፡ ገንዘብ ፡ አያበድር ። ሁለቱም ፡ ቢያበድሩ ፡ በሚገባ ፡ ጊዜ ይከፈሉ ። የሚያሳድጉት ፡ ሕፃን ፡ እካለ ፡ መጠ ንና ፡ አእምሮ ፡ እስኪያደርስ ፡ ድረስ ፡ አያዘግ ዩት ።

፩ሺ.፸፯ በሞግዚት ፡ ፊት ፡ ምስክር ፡ በመጥራት ፡ በገን ዘቡ ፡ ሁሉ ፡ እስተዳዳሪ ፡ ያደረጉት ፡ ሰው ፡ ምስክር ፡ የሚሆነው ፡ መጋቢ ፡ ከሌለ ፡ ፍርድ ሊጠይቅ ፡ አይገባውም ። ሞግዚት ፡ በሕይወት ፡ ባለበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ትእዛዝ ፡ እንደመታ ዘዙ ፡ ሞግዚት ፡ አይራቅ ። እንደዚሁም ፡ ስለመ ሻሩ ፡ ምስክር ፡ መጥራት ፡ ይገባል ። ሥራውም ይጸና ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ በዳኛ ፡ ዘንድ ፡ መግ ለጽ ፡ ነው ። ሕይወቱ ፡ ሳያልፍ ፡ በሁሉም ትእዛዝ ፡ ለሞግዚት ፡ ትሁን ።

፩ሺ.፸፰ በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ተጻፈ ፡ ለእግዚአብሔር ብለው ፡ ለወላጆቻቸው ፡ ላያቶቻቸው ፡ ለአባ ቶች ፡ ወንድሞችና ፡ እህቶች ፡ ለእናቶች ፡ ወን ድሞችና ፡ ለእናቶች ፡ እህቶች ፡ ከእነርሱም ፡ ወገን ፡ በደዌ ፡ ወይም ፡ አእምሮ ፡ በመጉደል ፡ ለተፈተነ ፡ ሁሉ ፡ ወይም ፡ ጉስቁልና ፡ ላገኘው ፡ ሰው ፡ መልካም ፡ ሊያደርጉ ፡ ለክርስቲያኖች ፡ ይገባል ። ከእርሷ ፡ የሚበልጥ ፡ የሚያንስም ፡ ቢሆን ፡ በሥራቸው ፡ ይተኩ ። እንደዚኹውም ፡ ሚስቶቻቸውን ፡ ባሮቻቸውንና ፡ ወዳጆቻቸውን ሊያስተካክሏቸው ፡ ይገባል ። ይኸውም ፡ ሐዋ ርያ ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ ቃል ፡ ይገባል ። ዘመ ዶች ፡ ያሉት ፡ ስለሚበጃቸው ፡ ነገር ፡ የማያስብ እርሱ ፡ ሃይማኖቱን ፡ ካደ ። ካላመኑም ፡ ሰዎ ች ፡ እርሱ ፡ ይከፋል ። (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፭ ፡ ፰) ።

## አንቀጽ ፴ወ፫ቱ ።

በእንተ ፡ ተማይጦ ፡ ወሠይጥ ፡ ወዘይትልዎሙ ።

፩ሺ.፸፱ ወውእቱ ፡ ፯ቱ ፡ ምዕራፍ ፡ እምአብጥሊስ ፡ ፲ወ፬ቱ ፡ ወእምቀኖና ፡ ነገሥት ፡ ካልእ ፡ መከ ፡ ዘ፳ወ፯ቱ ፡ ዘ፳ወ፯ቱ ፡ ዘ፳ወ፰ቱ ፡ ዘ፴ወ፪ቱ ፡ ዘ፴ ፡ ዘ፴ወ፩ዱ ፡ ወዘሂ ፡ ተወሰከ ፡ ላዕለ ፡ ዝንቱ ።

፩ሺ.፹ ምዕራፍ ፡ ቀዳማዊ ። ተማይጦስ ፡ ኢትትከውን ፡

## አንቀጽ ፡ ፴፫ ።

ስለመግዛትና ፡ ስለመሸጥ ፡ ስለሚከተላቸውም ፡ ይናገራል ።

፩ሺ.፸፱ ይኸውም ፡ ፯ ፡ ምዕራፍ ፡ ነው ። ከአብጥሊስ ፡ ፲፬ ፡ ከሁለተኛ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ መከ ፡ ፳፯ ፡ ፳፯ ፡ ፳፰ ፡ ፴፪ ፡ ፴ ፡ ፴፩ ። በዚህም ፡ ላይ ፡ ከተ ጨመረው ፡ የተገኘ ፡ ነው ።

፩ሺ.፹ መጀመሪያው ፡ ምዕራፍ ። ሻጭና ፡ ገዥ ፡ በገን

አማን ፡ ዘእንበለ ፡ ለእመ ፡ ኮኑ ፡ ሠያጢ ፡ ወተ ማያጢ ፡ ብዉሓነ ፡ ላዕለ ፡ ንዋዮሙ ፡ ወእመ ፡ ኢተሰነአዉ ፡ በአእምሮ ፡ ወዘኢኮኑ ፡ ታሕተ ፡ ምግብና ። ወኢትትፌጸም ፡ ሠይጥ ፡ ወተሣይጦ ዘእንበለ ፡ በመጥዎ ፡ ሠያጢ ፡ መላኪ ፡ ወተወክ ፎተ ፡ ተሣያጢ ፡ ዘእንበለ ፡ ትስግልት ። ወክል ኤሆሙ ፡ ኢይሰነአዉ ፡ ዘእንበለ ፡ ካልእ ፡ ብእሲ ዘኀረይዎ ፡ ለእመ ፡ ኢሐሰበ ። ወለእመ ፡ ሠምረ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ይኩን ፡ በሥምረተ ፡ ካልኡ ፡ ለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ይፈጽም ፡ ወለእመ ፡ ኢፈቀደ፡ ይሥዐር ። ወለእመ ፡ ተፈልጡ ፡ እምቅድመ ፡ ይሰነአዉ ፡ ላዕለ ፡ ሤጥ ፡ ተፀርዐት ፡ አው ፡ ተወ ከፎተ ፡ ተሣያጢ ፡ ወመጥዎተ ፡ ሠያጢ ፡ እስመ ዘይሠይጥ ፡ ወዘይሣየጥ ፡ ፪ኤሆሙ ፡ በሥምረ ቶሙ ፡ ውእቱ ።

፩ሺ.፹ ወኢይከውን ፡ ዘይትፌጸም ፡ በስምዕ ፡ ወኢበሥ ምረት ፡ በሠይጦ ፡ ንዋይ ፡ ዘኢዘለወ ፡ በከዋ ኔሁ ፡ ወለእመ ፡ ተዐውቀ ፡ ከዋኔሁ ፡ ተፈጸመ ፡ ተሣይጦ ፡ ወእመ ፡ እኮሰ ፡ በሥምረተ ፡ ተሣ ያጢ ፡ በብሂለ ፡ እሆ ፡ ወእብጥሎ ፡ ወተመጥዎ ፡ በዘያፈልስዎ ፡ ከመ ፡ ይፍልስ ፡ ለእመ ፡ ፈለሰ ፡ ተሠያጢ ፡ በእፍልሶተ ፡ ዘተሣየጦ ፡ እመካኑ ፡ አው ፡ በተእምኖቱ ፡ ከመ ፡ ያፍልሶ ፡ ኀበ ፡ ምልክናሁ ፡ ዘከመ ፡ እንስሳ ፡ ወእግብርት ፡ ወእለ ፡ ይትበልዑ ፡ ዘበበያታሆሙ ፡ ወእለ ፡ ይስትዩ ፡ ኪያሆሙ ፡ ወእለሂ ፡ ይለብስዎሙ ። ወሰዐውሂ ፡ ወመዛግብታት ፡ ወዘይትሜጠ ውዎ ፡ በእድ ፡ ተመጥዎ ፡ በሰንቈ ፡ ባሕርዮ ፡ ወዘአንሀብዎሂ ፡ ወዘይመስሎ ፡ ለዝንቱ ፡ እምነ ፡ ሥርጋዌ ፡ ወይትአመኑ ፡ ጠይቆተ ፡ እእምሮቶሙ ፡ ባቲ ፡ ዘከመ ፡ እዕፃድ ፡ ወገነ ታት ፡ ወምድር ።

፩ሺ.፹፩ ወተሣይጦሰ ፡ ወሤጥ ፡ ቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘይከ ውን ፡ በጽሒፍ ፡ ወቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ጽሒፍ ። ወዘሂ ፡ ይከውን ፡ በጽሒፍ ፡ ፍጹሜ ፡ ሁኒ ፡ ከመ ፡ የሀሉ ፡ በእደ ፡ ተሣያጢ ፡ መጽሐፍ ዘውስቴቱ ፡ ስምዐ ፡ ፪ቱ ፡ ስማዕት ፡ አው ፡ ፫ቱ፡ አው ፡ ዘይበዝኁ ፡ እመኒ ፡ በጽሐፈተ ፡ ፩ዱ ፡ እምስማዕታት ፡ አው ፡ በጽሕፈተ ፡ ሠያጢ ፡ አው ፡ በጽሐፈተ ፡ ጸሓፊ ፡ ዘይተልዎ ፡ ጽሕ ፈተ ፡ ሤጥ ። ወዘይነግር ፡ መጽሐፉ ፡ ተሰናእ ዎተ ፡ ሤጥ ፡ ወውስንየቲሃ ፡ ወከዋኔ ፡ ንዋይ ፡ ዘይሠይጥዎ ፡ ወመጠነ ፡ ሤጡ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡

ዘባቸው ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ ካልሆኑ ፡ በቀር ፡ መገበያየት ፡ እውነተኛ ፡ አትሆንም ። በዕውቀት ፡ ካልተስማሙ ፡ ከመተዳደር ፡ ሥር፡ ካልሆኑ ፡ ገዥ ፡ ለሻጭ ፡ በመስጠት ፡ ገዥም ፡ ያለቅሚያ ፡ በመቀበል ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ መሸጥ ፡ መግዛት ፡ አትፈጸምም ። የመረ ጡት ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ካልተቆጣጠረ ፡ ሁለቱ ፡ አይስማሙም ። ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ በአንደኛው ፡ ፈቃድ ፡ እንዲሆን ፡ ከወደደ ፡ ቢወድ ፡ ይፈጽም ባይወድ ፡ ይሻር ። ከመስማማታቸው ፡ በፊት ፡ በዋጋ ፡ ቢለያዩ ፡ ትቀራለች ። ወይም ፡ የገዥ ፡ መቀበልና ፡ የሻጭ ፡ መስጠት ፡ የሚሸጥና ፡ የሚገዛ ፡ ሁለቱ ፡ በፈቃዳቸው ፡ ነውና ።

፩ሺ.፹ በጨዋጌ.ታው ፡ የሌለ ፡ ገንዘብን ፡ በመሸጥ ፡ ጊዜ ፡ በምስክርና ፡ በመውደድ ፡ የሚፈጸም ፡ አይሆንም ። ጨዋጌታው ፡ ከታወቀ ፡ መሻሻጥ ፡ ተፈጸመ ። ያስዚያ ፡ ግን ፡ እሺ ፡ ወይም ፡ እንቢ ፡ ቢል ፡ በገዥ ፡ ፈቃድ ፡ ነው ። የገዛውን ፡ ከቦ ታው ፡ በማዛወር ፡ ወይም ፡ ወይማዛቱ ፡ (እጅ ነቱ) ፡ ያዛውረው ፡ ዘንድ ፡ በመተማመኑ ፡ ገዥ፡ ከቦታው ፡ ቢዛወር ፡ ይዛወር ፡ ዘንድ ፡ በሚወስ ዱት ፡ ገንዘብ ፡ መቀበል ፡ ነው ፡ ይኸውም ፡ እንደ ፡ እንስሳ ፡ እንደ ፡ ባሮች ፡ በየወገናቸው ፡ እንደሚበሉና ፡ እንደሚጠጡ ፡ እንደሚለብሷ ቸው ፡ እንደእንጨቶች ፡ እንደማጥሮች ፡ መቀ በልን ፡ በእጅ ፡ እንደሚቀበሉት ፡ እንደሰንቆና፡ እንደእነጠሩትም ፡ ከጌጥ ፡ ወገን ፡ ይሆን ፡ እንደ መሰለው ፡ ያለ ፡ ነው ። እርሷንም ፡ አውቀው ፡ መረዳትን ፡ ያመኑ ። ይኸውም ፡ እንደቦታ ፡ እንደ ፡ ተክል ፡ እንደ ፡ ምድር ፡ ያለ ፡ ነው ።

፩ሺ.፹፩ መግዛትና ፡ መሸጥ ፡ ከእነርሱ ፡ ወገን ፡ በጽሕ ፈት ፡ የሚሆን ፡ አለ ። ከእነርስም ፡ ወገን ፡ ያለ ጽሕፈት ፡ የሚሆን ፡ አለ ። በጽሑፍ ፡ የሚሆ ነው ፡ መጨረሻው ፡ በውስጡ ፡ ሁለት ፡ ወይም፡ ሦስት ፡ ወይም ፡ የሚበዙ ፡ ምስክሮች ፡ ያሉት ፡ ደብዳቤ ፡ በገዥ ፡ እጅ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ከምስክሮቹ ፡ አንዱ ፡ በጻፈውም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ሻጭ ፡ በጻፈው ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ዋጋን መጻፍ ፡ የሚገባው ፡ ጸሓፊ ፡ ቢጽፈው ። መጽሐፉም ፡ የሚናገር ፡ የዋጋውን ፡ ስምም ነትና ፡ ውሎቿን ፡ የሚሸጡትን ፡ ገንዘብ ፡

በውእቱ ፡ ጊዜ ፡ አው ፡ በሰደሚ ፡ ወመጠኑ ፡
ለሰደሚ ።

፩ሺ.፹፪ ወዘሂ ፡ ኮነ ፡ ዘእንበለ ፡ መጽሐፍ ፡ ይኩን ፡ በን
ግሊእ ፡ ዓረቦን ፡ ወዘእንበለ ፡ ዓረቦን ፡ ወተወክ
ፎቱ ፡ ሠያጢ ፡ ዓረቦነ ፡ እምእደ ፡ ተሣያጢ ፡
ይመርሖ ፡ ኀበ ፡ ፍጻሜ ፡ ሠይጥ ፡ ወተሣይጦ ።
ወለእመ ፡ ነሠተ ፡ ተሣያጢ ፡ ከዊነ ፡ ሣጥ ፡ ይኩ
ውን ፡ ዓረቦኑ ፡ ለሠያጢ ፡ ወእመሰ ፡ ለሊሁ ፡
ሠያጢ ፡ ሠዐረ ፡ ይፍዲ ፡ ካዕበተ ፡ ዓረቦኑ ፡
ወያግብእ ፡ ለበዓሉ ፡ ወየሀብ ፡ ኪያሁ ፡ ወእም
ሳሊሁ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘይሠይጥዎ ፡ በሣጥ ፡
በጽሐ ፡ እመንገሌሁ ፡ በውናይ ፡ ፍጻሜ ።

፩ሺ.፹፫ ወፍጻሜሁሰ ፡ ለሣጥ ፡ ተመጥዎቱ ፡ ተሣያጢ ፡
ኪያሁ ፡ ወመጥዎቱ ፡ ሲሣሁ ፡ ለሠያጢ ። ወእ
መኒ ፡ ኮነ ፡ ሣጠ ፡ ዘአሁ ፡ በሰደሚ ፡ ዘኢተ
ፈጸመ ፡ ኢየኀፍእ ፡ ተሣያጢ ፡ ኀዋየ ፡ እስከ ፡
ይትመተር ፡ ፈቃዱ ፡ ለሠያጢ ፡ ወይትፈጸም ፡
ተሰናእዎቶሙ ፡ ወእመ ፡ አኮ ፡ ሀየንተ ፡ ፈቃደ፡
አእምሮቶሙ ። ወተወልጦ ፡ ኢይትፈቀድ ፡ ኀበ
ምዕንያ ፡ ወኢ ፡ ኀበ ፡ ምዕኑ ፡ ሣጥ ፡ ወምዕኑ ፡
ዘእያሁ ፡ ኢኮነ ፡ ከመ ፡ ፍጻሜሁ ፡ ለምጣኔ ፡
ሣጥ ።

፩ሺ.፹፬ ወይደሉ ፡ አእምሮተ ፡ ዝንቱ ፡ ተዳማዊ ፡ ዘይት
ፈቀድ ፡ ኀበ ፡ ጥዩቅ ፡ ያታሃ ፡ ወመዝገቢሁ ፡ ወይ
በል ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ በዲናረ ፡ ወርቅ ፡ ፩ ፡
ንእስት፡ አው ፡ ዐቢይት ፡ ግብጻዊ ፡ አው ፡ ጢሮ
ሳዊ ፡ ወበጠፋልሐ ፡ ብሩር ፡ አው ፡ እምጽሩይ ፡
ወእምርሱሕ ፡ ዘተጽሕፈ ፡ በናዝሬት ፡ በከመ ፡
እበውሐ ፡ መጽሐፍ ። ወለእመ ፡ ኢተሰነአዉ ፡
በነገሮሙ ፡ ሣጠ ፡ መጠለያን ፡ ዘሀገር ፡ ይመ
ውእ ፡ ወፈድፋደሰ ፡ በነገሮሙ ፡ ለስብእ ፡
ይእቲ ፡ ሀገር ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ተውላጠ ፡
ብሩር ፡ ዘኢየኀብር ፡ ወኢይትዓረይ ፡ በአር
አያ ፡ ኢይትፈጸም ፡ ሠይጥ ፡ ወተሣይጦ ፡
እስከ ፡ ይትዐወቅ ፡ ከዊነ ፡ ተውላጠ ፡ ብሩር ።

፩ሺ.፹፭ ወዘይደሉ ፡ ለሠያጢ ፡ በተፈልጦ ፡ ወይበል ፡
በምድርኒ ፡ ወበፍሬሃ ፡ አው ፡ ዘእንበለ ፡ ፍሬሃ፡
አው ፡ ፍሬሃኒ ፡ ባሕቲቶ ፡ ወከማሁ ፡ ለዐውኒ ።
ወእመኒ ፡ አብሐ ፡ ልሳነ ፡ መጽሐፍ ፡ ውእቱ ፡
ዓፀደ ፡ ወእመኒ ፡ ኀደገ ፡ ነገረ ፡ እዕፃደ ፡ ይባእ ፡

ሁኔታ ፡ የዋጋውን ፡ ልክ ፡ በዚያው ፡ ጊዜ ፡
ወይም ፡ በቀጠሮ ፡ ቢሆን ፡ የቀጠሮውን ፡ ልክ ፡
ነው ።

፩ሺ.፹፪ ያለጽሑፍም ፡ የሚሆነው ፡ አረቦን ፡ (ቀብድ) ፡
በመቀበል ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ ዓረቦን ፡ (ቀብድ) ፡
ይሁን ። ሻጭ ፡ ከገዥ ፡ እጅ ፡ ዓረቦን ፡ (ቀብድ)፡
መቀበሉ ፡ ወደመሸጥና ፡ ወደመግዛት ፡ ፍጻሜ ፡
ይመራል ። ገዥ ፡ የዋጋውን ፡ ሁኔታ ፡ ቢያፈ
ርስ ፡ ዓረቦኑ ፡ (ቀብዱ) ፡ ለሻጭ ፡ ይሆናል ።
ራሱ ፡ ሻጭ ፡ ውሉን ፡ ቢሽር ፡ ዐረቦኑን ፡ (ቀብ
ዱን) ፡ እጥፍ ፡ አድርጎ ፡ ይክፈል ። ለባለቤቱም፡
ይመልስ ፡ ዓይነቱንና ፡ መለሱንም ፡ ይስጠው ።
በዋጋ ፡ የሚሸጡት ፡ ከሆነ ፡ ከእርሱ ፡ ወደመ
ልካም ፡ ፍጻሜ ፡ ደረሰ ።

፩ሺ.፹፫ የዋጋ ፡ ፍጻሜስ ፡ ገዥ ፡ እርሱን ፡ መቀበሉና ፡
ለሻጭ ፡ ዋጋውን ፡ መስጠቱ ፡ ነው ። ዋጋውም ፡
ያልተፈጸመ ፡ በቀጠሮ ፡ ቢሆን ፡ የሻጭ ፡
ፈቃድ ፡ ቁርጥ ፡ እስኪሆንና ፡ ስምምነታቸውም
እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ገዥ ፡ ገንዘቡን ፡ አያጥፋ ።
ያለዚያም ፡ ስለእውቀታቸው ፡ ፈቃድ ፡ ይሁን ።
ወደዓይነቱ ፡ ልክ ፡ ወይም ፡ ወደዋጋዋ ፡ ልክ ፡
መለወጥ ፡ አይፈቀድም ። የእርሱ ፡ ግምት ፡ እን
ደዋጋው ፡ ግምት ፡ ፍጻሜ ፡ አይሆንም ።

፩ሺ.፹፬ አስቀድሞ ፡ የሚፈለገው ፡ የዓይነቱንና ፡ የሚ
ዛኑን ፡ እርግጠኛነት ፡ ይህን ፡ ማወቅ ፡ ይገ
ባል ። በወርቅ ፡ ዲናር ፡ ፩ ፡ ቢሆን ፡ ትንሽ ፡
ወይም ፡ ትልቅ ፡ ግብጻዊ ፡ ወይም ፡ ጢሮሳዊ ፡
ነው ፡ ይበል ። በብር ፡ ሚዛንም ፡ ቢሆን ፡ ከጽ
ሩይ ፡ ወይም ፡ ከርሱሕ ፡ የተሠራ ፡ በናዝሬት ፡
የተጻፈ ፡ ነው ፡ ይበል ። መጽሐፍ ፡ እንደሚፈ
ቅደው ። በነገራቸውም ፡ ባይስማሙ ፡ የሀገር ፡
ነጋዴዎች ፡ ዋጋ ፡ ያቸንፋል ። ይልቁንም ፡
በዚያችው ፡ ሀገር ፡ ሰዎች ፡ ነገር ፡ ይሁን ።
የብሩ ፡ ልዋጭ ፡ በመልክ ፡ የማይመሳሰልና ፡
የማይተካከል ፡ ቢሆን ፡ የብሩ ፡ ለውጥ ፡ እኳ
ኋን ፡ እስኪታወቅ ፡ ድረስ ፡ መሸጥና ፡ መግ
ዛት ፡ አይፈጸምም ።

፩ሺ.፹፭ ለሻጭ ፡ የሚገባው ፡ በመለየት ፡ ምድሩንም ፡
ፍሬውንም ፡ ወይም ፡ ያለፍሬዋ ፡ ወይም ፡ ፍሬ
ዋን ፡ ብቻ ፡ ሽጬለሁ ፡ ይበል ። ዕንጨትም ፡
እንደዚሁ ፡ ነው ። የደብዳቤው ፡ ቃል ፡ ቦታ
ውን ፡ ቢፈቅድ ፡ የቦታውንም ፡ ነገር ፡ ቢተው ፡

ለሐኒፆታ ፡ ዘተማየጠ ፡ ወዝንቱኒ ፡ ወዘእ ምሳሊሁ ፡ ይኩን ፡ በከመ ፡ ተዐውቀ ፡ ኀበ ፡ ሰብእ ። ወሁቀትሰ ፡ ዘይስነአወ ፡ ላዕሌሁ ፡ በሢጥ ፡ ይጸንዕ ፡ ወለእመ ፡ ተሠይጠ ፡ ተክል ፡ ወቦቱ ፡ ፍሬ ፡ በዘማሰ ፡ እኢያገብርዎ ፡ ለተማ ያጢ ፡ አፍልሶቶ ፡ ወኢይክልእዎ ፡ ወሰቅዮቶ ፡ ወተሰናእዎተ ፡ ሀልዎቱ ፡ ወሰቅዮቱ ። እው ፡ አፍልሶቱ ፡ ይጸንዕ ። ወለዘሂ ፡ ይስፍርዎ ፡ ወይሜጥንዎ ፡ ወይደልዎ ፡ በመዳልው ፡ ይደሉ ፡ ሢጡ ፡ ወተማያጦቱ ፡ ገሃደ ፡ ወመ ዳልውኒ ፡ ወዘይትሜጠን ፡ በእመት ፡ ወዘ ይሰፈርሂ ፡ ይኀድስ ።

፩ሺ.፻፺፪ ወእመቦ ፡ ዘተማየጠ ፡ ልብሰ ፡ ለለ፩ዱ ፡ እመት፡ በ፩ዱ ፡ ድርኅም ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይማየጥ ፡ ኵለንታሁ ፡ እው ፡ ዘፈቀደ ፡ እምኔሁ ፡ በመ ጠነ ፡ ውእቱ ፡ ሢጥ ። ወእመኒ ፡ ተማየጣ ፡ ወኮነ ፡ እምጣኒሃ ፡ ፲ቱ ፡ በእመት ፡ ይማየጥ ፡ በ፲ቱ ፡ ድርኅም ። ወእመኒ ፡ ኮነት ፡ ዘተሐጽጸ፡ ድልው ፡ ሎቱ ፡ ሥምረት ፡ ወለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ይንሣእ ፡ ኪያሃ ፡ በሐሳበ ፡ ሢጡ ፡ ለእመ ፡ ሠምረ ፡ ሠያጢ ፡ ወለእመ ፡ ኢፈቀደ ፡ ይሠ ዐር ፡ ተማይጦ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘይበዝኅ ፡ ይኩን ፡ በሥምረተ ፡ ፪ሆሙ ፡ በእንተ ፡ ዘፈድ ፈደ ፡ እም፲ት ፡ ባሕቲቱ ።

፩ሺ.፻፺፫ ወእመቦ ፡ ዘርእየ ፡ ምንተኒ ፡ እምንዋዩ ፡ እንዘ ፡ ይሠይጥዎ ፡ በእደ ፡ ካልኡ ፡ ወተክህሎ ፡ ከመ ፡ ይክልእ ፡ ወኢተናገረ ፡ ይከውን ፡ ዘከመ ፡ ለሊሁ ሤጠ ፡ ወይደልዎ ፡ ለገብሩኒ ፡ ከመ ፡ ይማየጥ ፡ ወዘተማየጠሂ ፡ ይኩን ፡ ለእግዚኡ ።

፩ሺ.፻፺፬ ምዕራፍ ፡ ዳግማዊ ፡ ወለእመ ፡ ማስነ ፡ ዘተሠ ይጠ ፡ እምቅድመ ፡ ፍጻሜ ፡ ሠይጥ ፡ እመኒ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ ለዘተማየጦ ፡ ወእመኒ ፡ እ.ዘ ለወ ፡ እመ ፡ ኮነ ፡ ተማያጢ ፡ ዘአማሰኖ ፡ ይኩን፡ ሎቱ ፡ ወይእኅዝ ፡ ዕዳ ፡ ወይደልዎ ፡ ለሠያጢ ፡ ሢጡ ፡ በከመ ፡ ተሰነአወ ፡ ቅድመ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ካልእ ፡ ዘአማሰኖ ፡ ይፈዲ ፡ ዘየንቲሁ ፡ ወይኅረይ ፡ ተማያጢ ፡ እመኒ ፡ ለአብጥሎ ፡ ወእመኒ ፡ ለአቅሞ ፡ ወሠያጢሂ ፡ ይትኀሠሥ ፡ ለዘአማሰነ ፡ በመጠነ ፡ ሢጡ ። ወለ እመ ፡ ጠፍአ ፡ እምድኅረ ፡ ፍጻሜ ፡ ተማ ያጦ ፡ እመኒ ፡ ኮለንታሁ ፡ አው ፡ መንፈቁ ፡ ይኩን ፡ ለዘተማየጦ ፡ ወየሀብ ፡ መጠነ ፡ ሤጡ ፡ ለሠያጢ ፡ ወእመኒ ፡ ማስነ ፡ በዕለተ ፡ ተማይጦ።



የገዛ ፡ ሊሠራበት ፡ ይግባ ። ይህን ፡ የመሰለውም በሰው ፡ ዘንድ ፡ እንደታወቀው ፡ ይሁን ። የተሰ ማሙበት ፡ ዕውቀትስ ፡ በዋጋ ፡ ይጸናል ። ተክል ቢሸጥ ፡ በተሸጠው ፡ ተክል ፡ ፍሬ ፡ ቢኖርበት ፡ እንዲነቅለው ፡ ገዢውን ፡ እያስገድዱት ። ውሃ ፡ ከማጠጣት ፡ አይከልክሉት ። የመኖ ሩና ፡ ውሀ ፡ የማጠጣቱ ፡ ወይም ፡ ነቅሎ ፡ የመሄዱ ፡ መስማማት ፡ ይጸናል ። የሚሰፍሩ ትንና ፡ የሚለኩትን ፡ በሚዛን ፡ የሚመዘኑ ትንም ፡ በግልጽ ፡ መሸጥና ፡ መግዛት ፡ ይገ ባል ። የሚመዘነውና ፡ በክንድ ፡ የሚለካው ፡ የሚሠፈረውም ፡ ይሻላል ።

፩ሺ.፻፺፪ እያንዳንዱን ፡ ክንድ ፡ ልብስ ፡ በአንድ ፡ ድኅር ም ፡ የገዛ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ሁሉንም ፡ ወይም ፡ በዚያ ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፡ ከእርሱ ፡ የወደደውን ፡ ሊገዛ ፡ ይገባዋል ። ቢገዛትም ፡ ልኳ ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ ቢሆን ፡ በመቶ ፡ ድሪም ፡ ይግዛት ። ያነ ሰች ፡ ብትሆንም ፡ ለእርሱ ፡ ፈቃድ ፡ ይገባዋል። በዋጋው ፡ ሂሳብ ፡ እርሷን ፡ ሊወስድ ፡ ቢወድ ፡ ባይወድም ፡ መግዛቱ ፡ ይቀራል ። የሚበዛ ፡ ቢሆን ፡ ከመቶ ፡ ስለሚበዛ ፡ ብቻ ፡ በሁለቱ ፡ ፈቃድ ፡ ይሁን ።

፩ሺ.፻፺፫ ከገንዘቡ ፡ እንዳች ፡ በሌላው ፡ እጅ ፡ ሲሸጡት ፡ ያየ ፡ ቢኖር ፡ ሊከለክል ፡ ሲቻለው ፡ ባይናገር ፡ እርሱ ፡ እንደሸጠው ፡ ይሆናል ። ባሪያ ፡ ሊገበ ያይ ፡ ይገባዋል ። የገዛውም ፡ ለጌታው ፡ ይሁን ።

፩ሺ.፻፺፬ ሁለተኛው ፡ ምዕራፍ ፡ ከመሸጥ ፡ ፍጻሜ ፡ አስ ቀድሞ ፡ የተገዛው ፡ ቢጠፋ ፡ በገዢ ፡ እጅ ፡ ቢኖ ርም ፡ ባይኖርም ፡ ያጠፋው ፡ ገዢው ፡ ከሆነ ፡ በእርሱ ፡ ይሁን ። ዕዳም ፡ ይይዘዋል ፡ አስቀ ድሞ ፡ እንደተስማሙ ፡ ዋጋው ፡ ለሻጭ ፡ ይገ ባዋል ። ያጠፋው ፡ ሌላ ፡ ቢሆን ፡ ስለእርሱ ፡ ፈንታ ፡ ይከፈል ። ለመወሰንም ፡ ቢሆን ፡ ለማ ፍረስም ፡ ቢሆን ፡ ገዥ ፡ ይምረጥ ። ሻጭም ፡ በዋጋው ፡ ልክ ፡ እጥፊውን ፡ ይፈላለገው ። ከማገዛ ፡ ፍጻሜ ፡ በኋላ ፡ ቢጠፋ ፡ መላውም ፡ ቢሆን ፡ ግማሹም ፡ ቢሆን ፡ ለገዢው ፡ ይሁን ። በገዛበት ፡ ቀን ፡ ቢጠፋም ፡ የዋጋውን ፡ ልክ ፡ ለሻጭ ፡ ይስጥ ።

አንቀጽ ፡ ፴፫ ።

፩ሺ.፹፱ ወእመ ፡ ኮነ ፡ ሥዩጥ ፡ ገብረ ፡ ወማሰነ ፡ ምን ትኒ ፡ እምአባላቲሁ ፡ እመኒ ፡ እግሩ ፡ አው ፡ እዴሁ ፡ አው ፡ ዓይኑ ። ወእመኒ ፡ ኮነ ፡ ማኅደረ ፡ ወውዕየ ፡ ኵለንታሁ ፡ አው ፡ መንፈቁ ፡ ወእመኒ ፡ ኮነት ፡ ሀገረ ፡ ወኀለፈ ፡ ፈለግ ፡ ላዕሌሃ ፡ በኵለንታሃ ፡ አው ፡ ኀበ ፡ ፩ዱ ፡ መካን፡ እምኔሃ ፡ ወማሰነት ፡ አው ፡ ውሕደት ፡ አው ፡ ወድቁ ፡ አብያቲሃ ፡ አው ፡ አእዋሚሃ ፡ ወኵሉ ፡ ዘይከውን ፡ ዘከመ ፡ ዝንቱ ፡ እንዘ ፡ ኢይትዐወቅ ፡ ምንትኒ ፡ ጕሕሉት ፡ በላዕለ ፡ ሠያጢ ፡ ሀብተ ፡ ዚአሁ ፡ ውእቱ ፡ ለተሣያጢ ፡ ወይከውን ፡ ሠያጢ ፡ ድኁነ ፡ እምዕዳ ። ወከማሁ ፡ ኵሉ ፡ ዘተወለከ ፡ ውስተ ፡ ግብር ፡ ሥዩጥ ፡ እምንዋይ ፡ ዘይሠይጥዎ ፡ በክዋኔ ፡ ወበሜጥ ፡ ይከውን ፡ ለተሣያጢ ፡ ሀየንተ ፡ ሠያጢ ። ወለእመ ፡ ተንአዘ ፡ በእንተ ፡ አብጥሎቱ ፡ ይኩን ፡ በከመ ፡ ቃሉ ፡ ለሠያጢ ፡ ምስለ ፡ መሐላሁ ። ወእመኒ ፡ በውሳኔ ፡ ይኩን ፡ በከመ ፡ ቃሉ ፡ ለተሣያጢ ፡ ምስለ ፡ መሐላሁ ። እስከ ፡ ያመጽእ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ በጥያቄ ፡ ስማዕተ ፡ ወይፈትሑ ፡ ፍትሐ ፡ ዚአሆሙ ።

፩ሺ.፹፱ የተሸጠው ፡ ባሪያ ፡ ቢሆን ፡ ከሕዋሳቶቹ ፡ እግሩም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ እጁ ፡ ወይም ፡ ዐይኑ ፡ አንዳች ፡ ቢጎድል ፡ ቤትም ፡ ቢሆንና ፡ መላው ፡ ወይም ፡ እኩሌታው ፡ ቢቃጠል ፡ መን ደር ፡ ብትሆን ፡ ጎርፍ ፡ በእርሷ ፡ ላይ ፡ በመ ላዋ ፡ ወይም ፡ በእርሷ ፡ በአንዱ ፡ ቦታ ፡ በኩል ፡ ቢሄድባት ፡ ብትናድ ፡ ወይም ፡ ብትጕደጕድ ፡ ወይም ፡ ቤቶቿ ፡ ወይም ፡ ዛፎቿ ፡ ቢወድቁ ፡ በሻጭ ፡ ምንምን ፡ ተንኮል ፡ ሳይታወቅ ፡ እን ደዚህ ፡ የሚሆነው ፡ ሁሉ ፡ ለገዢ ፡ ገንዘቡ ፡ ነው ። ሻጭም ፡ ከዕዳ ፡ የዳነ ፡ ይሆናል ። እንደዚ ኸውም ፡ በፍጻሜና ፡ በዋጋው ፡ ከሚሸ ጡት ፡ ገንዘብ ፡ በሚሸጥ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ የተጨ መረው ፡ ሁሉ ፡ ስለሻጭው ፡ ፈንታ ፡ ለገዢ ፡ ይሆናል ። ስለማፍረስ ፡ ቢከራከሩ ፡ ከመሐላው፡ ጋር ፡ እንደሻጭ ፡ ቃል ፡ ይሁን ። በጭማሪም ፡ ቢሆን ፡ ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ በእርግጥ ፡ ምስክ ሮች ፡ እስኪያመጣ ፡ ድረስና ፡ ፍርዳቸውን ፡ እስኪፈርዱላቸው ፡ ድረስ ፡ ከመሐላው ፡ ጋር ፡ እንደገዥ ፡ ቃል ፡ ይሁን ።

፩ሺ.፺ ምስራፋ ፡ ሣልስ ፡ ወሠያጢ ፡ ለእመ ፡ ነገረ ፡ ይሢጥ ፡ ሎቱ ፡ ንዋየ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ሢጥኩ ፡ እነ ፡ እገሌ ፡ በጊዜሁ ፡ ለእገሌ ፡ በሤጠ ፡ እገሌ ፡ ወፍጻሜሁኒ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ሥምረቱ ፡ ለሠያጢ ፡ ወመማበቱ ፡ በሥምረተ ፡ ተሣ ያጢ ፡ እስከ ፡ ይፈትኖ ፡ የሀቦ ፡ ዕደሜ ፡ መጠነ ፡ ፫ቱ ፡ ዕለታት ፡ አው ፡ ዘይበዝኅ ፡ በዘ ኢይማስን ፡ ፍጡነ ። ወንዋይኒ ፡ ዘተሠይጠ ፡ የሀሉ ፡ በምልክናሁ ፡ ለሠያጢ ፡ በዕደሜ ፡ ኅሪ የት ፡ ወኢይደልዎ ፡ ይሥራዕ ፡ ውስቴቱ ፡ ዘእን በለ ፡ መባሕተ ፡ ተሣያጢ ፡ ወለእመ ፡ አስተባ ውሐ ፡ ወኢክልአ ፡ እምአስተዋዕኦቱ ፡ ተፈጸመ ኅሪየተ ፡ ሠያጢ ፡ ወይለዓ ፡ ሤጡ ። ወለእመ ፡ ሞተ ፡ ዘቦቱ ፡ ኅሪየት ፡ ተሠሰረት ፡ ተሣይጦ ።

፩ሺ.፺ ሦስተኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ሻጭ ፡ እኔ ፡ እገሌ ፡ በእገሌ ፡ ጊዜ ፡ በእገሌ ፡ ዋጋ ፡ ሸጥሁ ፡ ብሎ ፡ ሊሸጥለት ፡ ቢወድ ፡ ፍጻሜውም ፡ የሻጭ ፡ ፈቃድ ፡ እስኪፈ ጸም ፡ ድረስ ፡ መመገቡም ፡ በገዢ ፡ ፈቃድ ፡ ፈትኖ ፡ በማይጠፋ ፡ ገንዘብ ፡ እስኪፈትነው ፡ ድረስ ፡ ፫ ፡ ቀናት ፡ ያህል ፡ ወይም ፡ የሚበዛ ፡ ቀጠሮ ፡ ይስጠው ። የሸጠው ፡ ገንዘብም ፡ በም ርጫው ፡ ቀጠሮ ፡ በሻጭ ፡ እጅነት ፡ ይኑር ። ያለገዢ ፡ ፈቃድ ፡ በገንዘቡ ፡ ሊሠራበት ፡ አይገ ባውም ። ከፈቀደ ፡ ካልከለከለውም ፡ የሻጭ ፡ ምርጫ ፡ ተፈጸመ ። ዋጋውም ፡ ተገባው ። ምርጫ ፡ ያለበት ፡ ቢሞት ፡ ግን ፡ ሺያጭ ፡ ይቀ ራል ።

፩ሺ.፺፩ ወዘሂ ፡ ተሣየጠ ፡ ምንተኒ ፡ ዘከመ ፡ ሎቱ ፡ ግብር ፡ እሙር ፡ ወኢተረከበ ፡ ቦቱ ፡ ዘከመ ፡ ተሣየጠ ፡ ገብረ ፡ ዘከመ ፡ ውእቱ ፡ ኬንያ ፡ ወኢረከቦ ፡ ከማሁ ፡ ይኩን ፡ በኅሪየቱ ፡ ለተ ሣያጢ ፡ ለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ይንሥእ ፡ ወእመ ፡ ኢፈቀደ ፡ ይሚጦ ። ወከማሁ ፡ ለእመ ፡ ተሣ የጠ ፡ ምንተኒ ፡ ዘኢርእዮ ፡ ውእቱ ፡ አው ፡ መጋቢሁ ፡ ይኩን ፡ በከመ ፡ ኅረየ ። ወለእመ ፡

፩ሺ.፺፩ ምንም ፡ የገዛ ፡ ሰው ፡ ይኸውም ፡ የታወቀ ፡ ሥራ ፡ እንዳለው ፡ ያለ ፡ ነው ። ባይገኝበትም ፡ ይኸውም ፡ ብልሀ ፡ ነው ፡ የተባለ ፡ ባሪያን ፡ እንደገዛ ፡ ያለ ፡ ነው ፡ እንደተባለውም ፡ ባያገ ኘው ፡ ገዢ ፡ እንደ ፡ መረጠው ፡ ይሁን ፡ ቢወድ ይውሰደው ። ባይወድ ፡ ይመልሰው ፡ እንደዚ ሁም ፡ እርሱ ፡ ወይም ፡ መጋቢው ፡ ያላየውን ፡ አንዳች ፡ ነገር ፡ ቢገዛ ፡ እንደመረጠ ፡ ይሁን ።

በቍዖ ፡ ፩ዱ ፡ ክፍል ፡ በርእዩ ፡ ይንሥእሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ክፍል ፡ ዘእንበለ ፡ ርእዩ ፡ ዘከመ ፡ ዘይት ፡ ወእክል ፡ ወአልባስ ፡ ጥቅሉላት ፡ ወእመኒ ፡ ወጽአ ፡ ነውር ፡ እምቅድመ ፡ ሢጥ ፡ ወኮነ ፡ ሠያጢ ፡ ዘኢያእመረ ፡ ኪያሁ ፡ ወተሰነአወ ፡ ላዕሌሁ ፡ ዘኀረየ ፡ ተሣያጢ ፡ ይግበር ፡ ለንሣእኒ ፡ ወለኢንሣእኒ ፡፡ ወኢይደልዎ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይንሥእ ፡ በአሕጽጾ ፡ ዘእንበለ ፡ በሥምረተ ፡ ሠያጢ ፡፡

፩ሺ. ፺፪ ወለኵሉ ፡ ዘይደልዎ ፡ አሕጽጾተ ፡ ሤጥ ፡ ውስተ ፡ እእምሮተ ፡ ኀጢድ ፡ ነውር ፡ ውእቱ ፡ ዘከመ ፡ ስረቱ ፡ ግብር ፡ እው ፡ ጕያዩ ፡ እው ፡ ዘይሰይን ፡ ላዕለ ፡ መንጸፉ ፡ እው ፡ ዘየዐብድ ፡ እው ፡ ዘቦ ፡ ለምጽ ፡ በውሣጢ ፡ አባሉ ፡ እው ፡ ድዉየ ፡ አዕይንት ፡ ዘዘልፍ ፡ ወዘከመ ፡ ደዌ ፡ ዘይማስን ፡፡ ወዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ እንዘ ፡ ሀለወ ፡ ቦቱ ፡ በገብር ፡ ሶበ ፡ ሢጠ ፡ ይደልዎ ፡ ዕዳ ፡፡

፩ሺ. ፺፫ ወእምእንስሳኒ ፡ ለእመ ፡ ሢጠ ፡ ጥፉእ ፡ እንዘ ፡ የአምር ፡ ከመ ፡ ጋኔናዊ ፡ ውእቱ ፡ እው ፡ ዐብድ ፡ ለእመ ፡ ኢነገሮ ፡ ሠያጢ ፡ ለዘይሣየጥ ፡ ተብህለ ፡ ዕዳ ፡ በላዕሌሁ ፡፡ ወዘሢጠ ፡ ገብረ ፡ ወውእቱ ፡ እንዘ ፡ የአምር ፡ ከመ ፡ ፈያታዊ ፡ ውእቱ ፡ እው ፡ ዐብድ ፡ እው ፡ ዝንጉዕ ፡ ወኢነገሮ ፡ ለተሣያጢ ፡ ግዕዘ ፡ ዚአሁ ፡ ወፈድፋደሰ ፡ ለእመ ፡ ይቤ ፡ ጊዜ ፡ ተሰናእዎቱ ፡ አልቦ ፡ ውስቴቱ ፡ ነውር ፡ ሎቱኬ ፡ ይደልዎ ፡ በኑኀ ፡ ጊዜ ፡ አውሬኅ ፡ ከመ ፡ ያግብእ ፡ ወይትገነሠሥ ፡ በኵሉ ፡ ዘገብረ ፡ እምእተፍአቱ ፡ በውስተ ፡ ቤተ ፡ ተሣያጢ ፡፡ ወእመሰ ፡ ኀለፈ ፡ እምእሉ ፡ አውራኅ ፡ ወአንኰንዩዩ ፡ አልቦቱ ፡ ዕዳ ፡ ለሠያጢ ፡፡

፩ሺ. ፺፬ ወለእመ ፡ ጕየ ፡ ገብር ፡ እው ፡ እንስሳ ፡ በኑኀ ፡ ጊዜ ፡ አውራኅ ፡ ወኢጠንቀቀ ፡ ዐቂቦቶ ፡ የሀቦ ፡ ሢጦ ፡ ለዘሣጦ ፡፡ ወእመሰ ፡ ነገረ ፡ ጊዜ ፡ ይሠ ይጦ ፡ ከመ ፡ ገብር ፡ እኩይ ፡ ውእቱ ፡ ወከመ ፡ ውእቱ ፡ ኢያገብእ ፡ ኀቤሁ ፡ ኢይረክቦ ፡ ዕዳ ፡ ለአግብእቱ ፡ ወኢ ፡ ለፈድዮ ፡ ንዋዩ ፡ ለዘአበሰ ፡ ወኢ ፡ እግብእተ ፡ ሢጡ ፡ ወኢ ፡ በተንሥኦቱ ፡ ለእመ ፡ ጕየ ፡፡ ወለእመሰ ፡ ወዕአ ፡ ነውር ፡ ላዕለ ፡ ሥዩጥ ፡ በኑኀ ፡ ተሣያጢ ፡ ኢይደልዎ ፡ ለተሣያጢ ፡ ከመ ፡ የአኀዞ ፡ ለሠያጢ ፡ በአግብእተ ፡ ዚአሁ ፡ አላ ፡ ይደልዎ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ያግብእ ፡ ሕጸጸ ፡ ነውር ፡ ዘተረክበ ፡

በማየት ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ ቢበቃው ፡ እንደዚያው ፡ ክፍል ፡ ያለማየት ፡ ሁሉንም ፡ ይውሰዳቸው ፡፡ ይኸውም ፡ እንደ ፡ ዘይት ፡ እንደ ፡ እህል ፡ እንደተጠቀለሉ ፡ ልብሶች ፡ ያለ ፡ ነው ፡፡ ከዋጋ ፡ በፊት ፡ ነውር ፡ ቢወጣ ፡ ሻጭ ፡ ይህን ፡ ሳያውቅ የተዋዋለ ፡ ቢሆን ፡ ገዥ ፡ ለመውሰድም ፡ ለመተውም ፡ የመረጠውን ፡ ያድርግ ፡ ያለሻጭ ፡ ፈቃድ ፡ ዋጋውን ፡ በማዋረድ ፡ ሊወስደው ፡ አይገባውም ፡፡

፩ሺ. ፺፪ በንግድ ፡ ዕውቀት ፡ ውስጥ ፡ ዋጋን ፡ አጕድሎ ፡ መሸጥ ፡ የሚገባው ፡ ሁሉ ፡ ነውር ፡ ቢያገኝበት ፡ ነው ፡፡ ይኸውም ፡ እንደ ፡ ሌባ ፡ ባሪያ ፡ እንደ ፡ ኰብላይ ፡ ወይም ፡ ከምንጣፉ ፡ ላይ ፡ እንደሚሸን ፡ ወይም ፡ እንደሚያብድ ፡ ወይም ፡ በሰውነቱ ፡ ውስጥ ፡ ለምጽ ፡ እንደአለበት ፡ ወይም ፡ ዘወትር ፡ እንደዐይኑ ፡ በሽተኛ ፡ የሚጎዳ ፡ ደዌ ፡ እንዳለበት ፡ ያለ ፡ ነው ፡፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ በባሪያው ፡ እያለበት ፡ ቢሸጥ ፡ ዕዳ ፡ ይገባዋል ፡፡

፩ሺ. ፺፫ ከእንስሳትም ፡ ወገን ፡ ኰብላይ ፡ ጋኔናም ፡ እብድ ፡ እንደሆነ ፡ እያወቀ ፡ ቢሸጥ ፡ ሻጭ ፡ ለገዢ ፡ ባይነግረው ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ዕዳ ፡ አለ ፡ ተባለ ፡ ሽፍታ ፡ ወይም ፡ ሰነፍ ፡ ወይም ፡ ዝንጉዕ ፡ እንደሆነ ፡ እያወቀ ፡ ባሪያ ፡ የሸጠ ፡ ለገዢውም ፡ ጠባዩን ፡ ባይነግረው ፡ ይልቁንም ፡ በመስማቱ ፡ ጊዜ ፡ ነውር ፡ የለበትም ፡ ቢል ፡ በስድስት ፡ ወሩ ፡ ሊመልስለት ፡ ይገባዋል ፡፡ በገዥው ፡ ቤት ፡ ከማጥፋቱ ፡ የተነሣ ፡ ባደረገው ፡ ሁሉ ፡ ይፈላሰገው ፡፡ ከእሊህ ፡ ወራቶች ፡ ቢያልፍ ፡ ግን ፡ ቢያዘገየውም ፡ በሻጭ ፡ ዕዳ ፡ የለበትም ፡፡

፩ሺ. ፺፬ በስድስት ፡ ወር ፡ ስድሚ ፡ ባሪያው ፡ ወይም ፡ እንስሳው ፡ ቢኰበልል ፡ መጠበቁንም ፡ ባይጠነቀቅ ፡ ዋጋውን ፡ ለሸጠለት ፡ ይስጠው ፡፡ በሚሸጥበት ፡ ጊዜ ፡ ክፉ ፡ ባሪያ ፡ እንደሆነ ፡ ወደእርሱም ፡ የማይመለስ ፡ እንደሆነ ፡ ቢናገር ፡ ግን ፡ እርሱን ፡ ለመመለስ ፡ ባሪያው ፡ ያጠፋውን ፡ ገንዘብ ፡ ለመክፈል ፡ ዋጋውንም ፡ ለመመለስ ፡ ቢጠፋም ፡ እርሱን ፡ ለመፈለግ ፡ ዕዳ ፡ አያገኘውም ፡፡ በገዥ ፡ ዘንድ ፡ በተሸጠው ፡ ላይ ፡ ነውር ፡ ቢገኝበት ፡ ገዥ ፡ እርሱን ፡ ለመመለስ ፡ ሻጭን ፡ ሊይዘው ፡ አይገባውም ፡፡ በሻጭ ፡ ላይ ፡ የቀደመ ፡ የነውር ፡ ቅናሽን ፡ ያስ

እንቀጽ ፡ ፴፫ ።

ላዕለ ፡ ሠያጢ ፣ እመሰ ፡ ተገእዘ ፡ ፪ኤሆሙ ፡ ወኮነ ፡ ነውር ፡ እምዘይትከሀል ፡ ይኩን ፡ በከመ ቃሉ ፡ ለሠያጢ ፡ ምስለ ፡ መሐላሁ ። ወእመኒ ፡ እግብዐ ፡ አው ፡ ሞተ ፡ በኀቤሁ ፡ ኢይግባእ ፡ ሎቱ ፡ ምንትኒ ። ወከማሁ ፡ ለእመ ፡ መጽወቶ ፡ አው ፡ ወሀቦ ፡ አው ፡ ሤጦ ፡ ኢይገብእ ፡ ኀቤሁ ፡ አው ፡ ኮነ ፡ ገብረ ፡ ለዘኢኮነ ፡ ምእመን ፡ ወተሣየጦ ፡ ወአጥመቆ ። አው ፡ ኮነት ፡ አሐቲ ፡ አመት ፡ እንተ ፡ ተአምን ፡ ወአውሰበ ፡ ኪያሃ ፡ አው ፡ አስተዋሰባ ፡ ለ፩ዱ ፡ እምእመናን ፡ ወእሉ ፡ ግብራት ፡ ኵሎሙ ፡ ኢይገብኡ ፡ ወኢይመይጥዎሙ ፡ ኀበ ፡ ሠያጢ ፡ በእንተ ፡ ሕጸጸ ፡ ነውር ።

፩ሺ. ፺፮ ወለእመ ፡ ቦቱ ፡ ለሠያጢ ፡ ልብሰ ፡ ወሣጦ ፡ ወእመ ፡ ሴረዮ ፡ አው ፡ ገብሮ ፡ ቀሚሰ ፡ አው ፡ ሰፈዮ ፡ እምድኅረ ፡ ተሣየጠ ፡ ወፈቀደ ፡ ከመ ፡ ያግብእ ፡ ሎቱ ፡ ድኅነ ፡ ሠያጢ ፡ እምነውረ ፡ ዚአሁ ። ወኵሉ ፡ ዘአምሳሊሁ ፡ ለዝንቱ ፡ ፩ዱ ፡ ኵንኔሆሙ ።

፩ሺ. ፺፯ ወለእመ ፡ አእመረ ፡ ተሣያጢ ፡ ላዕለ ፡ ነውር ፡ ዘቀደመ ፡ ወተኰነኖ ፡ ተፋትሖ ፡ በእንቲአሁ ፡ ወኢገብረ ፡ ዘንተ ፡ ተመትረት ፡ ተኀሥሦቱ ። ወእመኒ ፡ ኀጢአ ፡ ለገብር ፡ ዘተሣየጦ ፡ ወቦቱ ፡ ነውር ፡ ዘቀደመ ፡ ዘኢያእመሮ ፡ ኪያሁ ፡ ወረ እዮ ፡ ተሣያጢ ፡ ዳግማዊ ፡ ኢይደልዎ ፡ ዕዳ ፡ ለተሣያጢ ፡ ቀዳማዊ ፡ በኀበ ፡ ፈታሒ ፡ በሰምዐ ፡ ጥይቁ ፡ እኩ ፡ በነገር ፡ ባሕቲቱ ፡ ውእቱ ፡ ይደልዎ ፡ የአኅዞ ፡ ለሠያጢ ፡ ቀዳማዊ ። ወለእመሰ ፡ ተሰነአዎ ፡ በምንትኒ ፡ ላዕለ ፡ ንዋይ ፡ ዘእንበለ ፡ ፈታሒ ፡ ኢይደልዎ ፡ ዕዳ ። ወኵሉ ፡ ዘተርእየ ፡ ነውረ ፡ ዚአሁ ፡ በጊዜ ፡ ሤጥ ፡ ኢይደልዎ ፡ ዕዳ ፡ በምንትኒ ፡ እምነውረ ፡ ዚአሁ ፡ ለእመ ፡ ፈለጠ ፡ ነውራተ ፡ ኵሎ ፡ በዘከር ፡ አው ፡ ኢፈለጠ ።

፩ሺ. ፺፰ ምዕራፍ ፡ ራብዕ ። በእንተ ፡ ዘኢይደሉ ፡ ሠይጠቱ ፡ ወኢተሣይጦቱ ። ወኢይደሉ ፡ ሠይጠ ፡ ግዑዛን ፡ ወኢሠይጠ ፡ ምእመናን ፡ ለእለ ፡ ኢኮኑ ፡ ምእመናን ፡ ወኢሠይጠ ፡ አዝማድ ፡ ወኢሠይጠ ፡ ወዓልት ፡ ግሙራ ፡ ወኢሠይጠ ፡ ዘጕለትዎ ፡ ወፈደፋደሰ ፡ ኢይሣጥ ፡ ገብረ ፡ ዘኢተነየ ፡ እምቀዳሚ ። ወኢይሣጥ ፡ ዘአማኅበ ንዎ ፡ በፍኖተ ፡ ማኅበራት ፡ ውክፍት ፡ ወተኖ

ስለ ፡ መሸጥና ፡ መግዛት ።

መልስ ፡ እንጂ ። ሁለቱ ፡ ቢከራከሩ ፡ ነውሩም ፡ ከማይቻል ፡ ወገን ፡ ቢሆን ፡ ከመሐላው ፡ ጋር ፡ እንደሻጭ ፡ ቃል ፡ ይሁን ። ነፃ ፡ ቢያወጣው ፡ ወይም ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ቢሞት ፡ ምንም ፡ አይመለሰለት ። እንደዚሁም ፡ ቢመጸውተው ፡ ወይም ፡ እሳልፎ ፡ ቢሰጠው ፡ ወይም ፡ ቢሸጠው ፡ ወደእርሱ ፡ አይመለስም ። ወይም ፡ ላላመነ ፡ ሰው ፡ ባሪያ ፡ ቢሆን ፡ ገዝቶም ፡ ቢያጠምቀው ፡ ወይም ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ባሪያ ፡ የምታምን ፡ ብትሆን ፡ እርሷንም ፡ ቢያገባት ፡ ወይም ፡ ከምእመናን ፡ ለአንዱ ፡ ቢያጋባት ፡ (ቢድራት) ፡ እኒህ ፡ ሁሉ ፡ ሥራዎች ፡ አይመለሱም ። በነውር ፡ ጉድለት ፡ ምክንያትም ፡ ወደ ሻጭ ፡ አይመልሷቸውም ።

፩ሺ. ፺፮ ለሻጭ ፡ ልብሰ ፡ ቢኖረውና ፡ ቢሸጠው ፡ ቀለምም ፡ ቢያገባው ፡ ቀሚስ ፡ ቢያደርገውም ፡ ከገዛው ፡ በኋላ ፡ ቢሰፋው ፡ ሊመልሰውም ፡ ቢወድ ፡ ሻጭ ፡ ከነውሩ ፡ ዳነ ። ይህን ፡ የመሰለው ፡ ሁሉ ፡ ፍርዳቸው ፡ አንድ ፡ ነው ።

፩ሺ. ፺፯ ገዥ ፡ የቀደመ ፡ ነውሩን ፡ ቢያውቅ ፡ ስለእርሱ ፡ ከእርሱ ፡ መፋረድ ፡ ሊቻለው ፡ ይህን ፡ ባያደርግ ፡ መፈላለጉ ፡ ትቀራለች ። የገዛውን ፡ ባሪያ ፡ ቢሸጠው ፡ እርሱ ፡ ያላወቀው ፡ የቀደመ ፡ ነውር ፡ ቢኖርበት ፡ ሁለተኛውም ፡ ገዥ ፡ ቢያየው ፡ በቃል ፡ ብቻ ፡ ያደደለ ፡ በማስረጃ ፡ ምስክር ፡ በዳኛ ፡ ዘንድ ። የፊተኛውን ፡ ገዥ ፡ ዕዳ ፡ አያገኘውም ። እርሱም ፡ የፊተኛውን ፡ ሻጭ ፡ ሊይዘው ፡ ይገባዋል ። በማናቸውም ፡ በገንዘብ ፡ ያለ ዳኛ ፡ ቢስማማ ፡ ግን ፡ ዕዳ ፡ አይገባውም ። በዋጋ ፡ ጊዜ ፡ የታየ ፡ ነውር ፡ ሁሉ ፡ ከነውር ፡ ወገን ፡ በማናቸውም ፡ ነውሮችን ፡ ሁሉ ፡ በመናገር ፡ ቢለይ ፡ ወይም ፡ ባይለይ ፡ ዕዳ ፡ አይገባውም ።

፩ሺ. ፺፰ ፬ኛው ፡ ምስራፍ ፡ ሊሸጡትና ፡ ሊገዙት ፡ ስለ ማይገባ ፡ ይናገራል ። ነፃ ፡ የወጡትንና ፡ ያመኑትን ፡ ላላመኑ ፡ ሰዎች ፡ መሸጥ ፡ አይገባም ። ዘመዶችን ፡ መሸጥ ፡ ሎሌዎችን ፡ ከቶ ፡ መሸጥ ፡ የጐለቱትንም ፡ መሸጥ ፡ አይገባም ። ይልቁንም ፡ ከጥንት ፡ ያልገዛውን ፡ ባሪያ ፡ አይሸጥ ። ተቀባይነት ፡ ባላት ፡ በአደራና ፡ በጠባቂነት ፡ መንገድ ፡ አደራ ፡ ያስጠበቁትንም ፡

አንቀጽ ፡ ፴፫ ።

ልዎ ፡ ወዘኢይክል ፡ ሣሰለ ፡ አወፋየት ፡ ዘከመ ፡
ግብር ፡ ኍያዪ ፡ ወንግ ፡ ዘውስተ ፡ ፈለግ ፡
ወሦፍ ፡ ዘይወርር ፡ ወወይጠል ፡ ዘየዐይል ፡
ውስተ ፡ ገዳም ፡ ወኢይሚጡ ፡ ምንተኒ ፡ ወኢ
ይማየጡ ፡ ግብረ ፡ ዘይኍይይ ፡ ወአሥጋሬ ፡ ዓሣ ፡
ዘባሕር ፡ ወአሥጋሬ ፡ ዖፍ ፡ ዘይወርር ፡ ወዘዩ
ንዑ ፡ ወይጠለ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ።

፩ሺ.፺፰ ወኢይከዮን ፡ ዓዲ ፡ ተማይጦ ፡ አው ፡ ለወልዐ ፡
ሕሩም ፡ ዘከመ ፡ ማውታ ፡ ወደም ፡ ወብላዐ ፡
አርዌ ፡ ወዘይወብሉ ፡ ለባሆት ፡ ወእንስሳት ፡
እለ ፡ ይትትሉ ፡ በሕምሆሙ ፡ ወአራዊት ፡ መግ
ተያን ፡ እለ ፡ ኢይሚንዩ ፡ ለንሰውት ፡ ወዘኢይበ
ቍዑ ፡ ባቲ ፡ በእንተ ፡ አሕሥሞ ፡ ዘይከውን ፡
እምነቢሃ ፡ ዘከመ ፡ ከይሲ ፡ ወአንበሳ ፡ ወዘከመ
በቀላት ፡ ቀታልያን ፡ ወዘተርፉሂ ፡ ዘዘእሙ ፡
እለ ፡ ይትትሉ ። ወኢ ፡ እለ ፡ ኢይበቍዑ ፡
ግሙራ ፡ ዘከመ ፡ ተሐዋስያን ፡ ወዘኢይትአ
መር ፡ በሰይሚ ፡ መጠነ ፡ ግጡ ፡ እምኀበ ፡
እስከ ፡ ጊዜ ፡ ውሂብ ፡ ወዘኢይትአመር ፡ እር
አያሁ ፡ ዘከመ ፡ ዕንስ ፡ ዘእንበለ ፡ እሙ ፡ ወኢ
ፍሬ ፡ እምቅድመ ፡ ታስተርኢ ፡ ወሐሊብ ፡
ዘውስተ ፡ ጥብ ፡ ወምስክ ፡ ዘውስተ ፡ ቢረሌ ፡
ወመዓር ፡ ዘውስተ ፡ ቀሰት ። ወኢይሠጥ ፡ ግብ
ራት ፡ ብጡሓት ፡ ስቱፋት ፡ ማእከለ ፡ ሰብእ ፡
ከመ ፡ ፍሬሆሙ ፡ ወግብር ፡ ወማያት ፡ እለ ፡ የሐ
ውሩ ፡ በምንትኒ ፡ እምኔሃ ፡ እምቅድመ ፡ ይፋ
ልሱ ፡ እመካናቲሆሙ ።

፩ሺ.፺፱ ወኢይሚጡ ፡ ዕንስተ ፡ ዘእንበለ ፡ ምስለ ፡ ዕንስ፡
ዚእሃ ፡ ወኢ ፡ ወሳዲተ ፡ ዘእንበለ ፡ ምስለ ፡
ወልዳ ፡ እምቅድመ ፡ ጎዲገ ፡ ጥብ ፡ በእንተ ፡
ተዓቅቦ ፡ እምተጓጕሎቱ ። ወኢ ፡ እምነ ፡ ዘይ
ደሉ ፡ ሣሰሊሁ ፡ ቀትል ፡ ወኢ ፡ ውሂበ ፡ ንዋየ ፡
ሐቅል ፡ ለአማሳንያን ፡ ዘከመ ፡ ውሂበ ፡ መጥ
ባሕት ፡ ለፈያታዊ ፡ ወውሂበ ፡ ስርፍ ፡ ለጕሕ
ላዊ ፡ ወውሂበ ፡ ማኅተም ፡ ዘወርቅ ፡ ለዘኢይ
ደሉ ።

፩ሺ.፻ ወሠኒጠ ፡ ንዋየ ፡ ዘኢይከውን ፡ እማን ፡ ውይ
ጡቱ ፡ ምስለ ፡ ዘይከውን ፡ እማን ፡ ዘከመ ፡
ሠይጠ ፡ ፪ቱ ፡ ዘከመ ፡ ውእቶሙ ፡ ፪ቱ ፡ እግ
ብርት ፡ ወተረክበ ፡ ከመ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡
እግአዚ ፡ ውእቱ ፡ ወተማይጦስ ፡ በነርየት ፡

ስለ ፡ መሸጥና ፡ መግዛት ።

መስጠት ፡ የማይቻለውንም ፡ ነገር ፡ አይሸጥ ።
ይኸውም ፡ እንደ ፡ ኵብሳይ ፡ ባሪያ ፡ በወንዝ ፡
ውስጥ ፡ እንዳለ ፡ ዓሣ ፡ እንደሚበር ፡ ወፍ ፡
በበርሀ ፡ እንደሚዞር ፡ ፈቆ ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ኵብሳይ ፡
ባሪያን ፡ ዓሣ ፡ አሥጋሪ ፡ የባሕሩን ፡ ወፍ ፡ አጥ
ማጅ ፡ የሚበረውን ፡ አዳኝም ፡ የበርሀውን ፡
ፈቆ ፡ አንዳችም ፡ አይሽጡ ፡ አይማዙም ።

፩ሺ.፺፰ ዳግመኛም ፡ የተከለከለውን ፡ መግዛት ፡ ወይም፡
መለወጥ ፡ አይሁን ። ይኸውም ፡ እንደበከት ፡
(ሙቶ ፡ እንዳደረ) ፡ እንደ ፡ ደም ፡ እንደ ፡ አውሬ
ትራፊ ፡ ለባዮት ፡ እንደተወጋ ፡ በመርዛቸው ፡
እንደ ፡ ሚገድሉ ፡ እንስሳት ፡ ለመታደን ፡ እንደ፡
ማይመቹ ፡ የሚነጥቁ ፡ አውሬዎች ፡ ከእርሷ ፡
የተገኘውን ፡ የሚጎዳ ፡ ስለሆነ ፡ የማይጠቀሙበ
ትን ፡ እንደ ፡ እባብና ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ እንደሚ
ገድሉ ፡ አዝርዕቶች ፡ ያሉ ፡ ናቸው ። በያይነቱ ፡
የቀሩትንም ፡ የሚገድሉትን ፡ ፈጽመው ፡ የማይ
ጠቅሙትን ፡ እንደ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ከዋጋም ፡
እስከ ፡ መስጠት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ የዋጋውን ፡
ልክ ፡ በቀጠሮ ፡ የማይታወቀውን ፡ ይኸውም ፡
እንደ ፡ ዕንስ ፡ ያለውን ፡ ያለእናቱ ፡ ወይም ፡
ከመታየቱ ፡ አስቀድሞ ፡ እንደ ፡ ፍሬ ፡ በጡት ፡
ውስጥ ፡ እንዳለ ፡ ወተት ፡ በብርሌ ፡ ውስጥ ፡
እንዳለ ፡ ሽቱ ፡ በማድጋ ፡ ውስጥ ፡ እንዳለ ፡ ማር ፡
ያለ ፡ ነው ። ወይም ፡ በሰዎች ፡ መካከል ፡ አንድ
ነት ፡ የተፈቀዱትን ፡ ነገሮች ፡ እንደ ፡ ጎዳና ፡ እን
ደ ፡ ማር ፡ ከእርሷ ፡ በማናቸውም ፡ በኩል ፡ እን
ደሚሄዱ ፡ ውሀዎች ፡ ከቦታው ፡ ሳይነሱ ፡
መሸጥ ፡ አይገባም ።

፩ሺ.፺፱ ያረገዘችውን ፡ ከእረገዘችው ፡ ጋር ፡ ካልሆነ ፡
የወለደችውንም ፡ ከልጅዋ ፡ ጋር ፡ ካልሆነ ፡
ጡት ፡ ከመጣሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ከጥፋቱ ፡ ሞትም
የሚገባው ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ስለመጠበቅ ፡
አይሽጡ ። ጥፋትን ፡ ለሚያደርጉ ፡ ሰዎች ፡
የጦር ፡ መሣሪያ ፡ መስጠት ፡ አይገባም ። ይኸ
ውም ፡ ለሽፍታ ፡ ሰይፍ ፡ እንደመስጠት ፡ ለሌባ
ድጅና ፡ እንደመስጠት ፡ ለማይገባው ፡ ሰው ፡
የወርቅ ፡ ማኅተም ፡ እንደመስጠት ፡ ያለ ፡ ነው ።

፩ሺ.፻ መሸጡ ፡ እውነተኛ ፡ ያልሆነውን ፡ ለቀ ፡ እው
ነተኛ ፡ ከሆነው ፡ ጋር ፡ የሸጠ ፡ ሁለቱን ፡ እንደ ፡
መሸጥ ፡ ያለነው ። እነዚህም ፡ እንደ ፡ ሁለት ፡
ባሮች ፡ ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ ነፃ ፡ እንደሆነ ፡
ቢገኝ ፡ ነው ። በምርጫ ፡ መግዛትስ ፡ በሚገባ ፡

በዘይደሉ ፡ ሠይጦቱ ፡ ቀዩቀ ። ወላዕለ ፡ ሠያጢ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ያግብእ ፡ ሎቱ ፡ ሤጠ ፡ በዘኢይከውን ፡ እማን ፡ ሠይጦቱ ። ወዘተሣየጠ ፡ ምንተኒ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ይጕልቆ ፡ አው ፡ ይመጽውቶ ፡ በቱ ፡ ያጥብዕ ፡ ለጕልቆቱ ፡ አው ፡ በመጽውቶ ፡ በቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ዳእሙ ፡ ለእመ ፡ ግብተ ፡ ነጥአ ፡ ዘይመልኮ ፡ ወነደየ ።

፩ሺ፩፻፩ ወዘሤጠ ፡ ዓፀደ ፡ ዘኢኮነት ፡ ዘዚአሁ ፡ ወሐነጸ ፡ ውስቴታ ፡ ዘተሣየጣ ፡ ሕንጸ ፡ ወለመላኪሃ ፡ ዘቀዳሚ ፡ ይኩን ፡ ኅርየት ። ወእመኒ ፡ ፈቀደ ፡ መጠነ ፡ ሤጥ ፡ ይንሣእ ፡ እምኍሕላዌ ፡ አው ፡ መጠነ ፡ ሤጣ ፡ እምነ ፡ ተሠያጢ ፡ ወእመኒ ፡ ፈቀደ ፡ ይኩን ፡ ሎቱ ፡ በውስተ ፡ ዓፀድ ፡ በእምጣነ ፡ ሤጣ ፡ እምቅድመ ፡ ትትሐነጽ ፡ ዘተረክበ ፡ ድኅረ ፡ እምሤጠ ፡ ዚአሃ ። ወይደሉ ፡ ለተሠያጢ ፡ ከመ ፡ ይኅረይ ፡ ለእመ ፡ ሠምረ ፡ በዝንቱ ፡ አው ፡ ያፍልስ ፡ ዘሐደሰ ፡ እምብልየቱ ወይንሣእ ፡ ለሤጥ ፡ ቀዳማዊ ፡ እምነ ፡ ዘተኀሕለወ ።

፩ሺ፩፻፪ ወትእዛዝሰ ፡ እልበ ፡ ውስቴቱ ፡ ከመ ፡ ይሣየጥ ፡ ንዋየ ፡ ሰራቅያን ፡ ወለዘእጽሐፉ ፡ ሎቱ ፡ ትእዛዘ ፡ ኢይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይሣየጥ ፡ ምንተኒ ፡ እምንዋየ ፡ ደካትም ፡ ወዘከመ ፡ ዝንቱኒ ፡ ይደልዎ ፡ ለመጋቢ ። ወኢይደልዎ ፡ ለመኑሂ ፡ እምሠዩማን ፡ ከመ ፡ ይሣየጥ ፡ እምነ ፡ ዘሀሎ ፡ ሥዩመ ፡ በላዕሌሁ ፡ አው ፡ እምነ ፡ ዘሀለወ ፡ ታሕተ ፡ ሢመቱ ፡ ምንትኒ ፡ እምተሐዋስያን ፡ አው ፡ እምእለ ፡ ኢይትሐወሱ ፡ ላዕለ ፡ እደ ፡ ማእከላዊ ፡ ወኢ ፡ በነፍሱ ፡ ዘእንበለ ፡ በመጠነ ፡ ሤጡ ፡ ወበሥምረቱ ፡ ለሠያጢ ። ወለእመ ፡ ገብረ ፡ ዘእንበለ ፡ ዝንቱ ፡ ይንሥኡ ፡ እምኔሁ ፡ ዘተሣየጠ ፡ ወኢያግብእ ፡ ሎቱ ፡ ሤጡ ። ወባሕቱ ፡ ይትፌለጥ ፡ ለእሠንዮታት ፡ ዘተለንታሁ ።

፩ሺ፩፻፫ ወኢይደሉ ፡ ነሢአተ ፡ ፈጽሞ ፡ ዘተሣየጦ ፡ በቃለ ፡ ውሳኔ ፡ ሙሴን ፡ ከመ ፡ ዘይብል ፡ ሶበ ፡ ትወልድ ፡ ዛቲ ፡ ላሕም ፡ ወወለደ ፡ ወልዳ ፡ ናሁ ፡ እሠይጥ ፡ ለከ ፡ ዘተወልደ ፡ አው ፡ ከመ ፡ ዘይብል ፡ ሤጥኩ ፡ ለከ ፡ ዘንተ ፡ ሀፀደ ፡ በ፶ ፡ በሥርዓት ፡ ውሳኔ ፡ ከመ ፡ ትሣጥ ፡ ሊተ ፡ ገብረከ ፡ በ፳ ። አው ፡ ከመ ፡ ዘይብል ፡ ሤጥኩ ፡ ለከ ፡ ዘንተ ፡ ገብረ ፡ በ፲ቱ ፡ ፍጡነ ፡ አው ፡ በ፳ በውሂበ ፡ ዕድሜ ።



መሸጡ ፡ የተረጋገጠውን ፡ ነው ። መሸጡ ፡ እውነተኛ ፡ ባልሆነው ፡ ነገር ፡ ዋጋውን ፡ ሊመልስለት ፡ ለሻጭ ፡ ይገባል ። እንደሚጐልተው ፡ ወይም ፡ እንደሚመጸውተው ፡ እድርጎ ፡ እንዳች ፡ ነገር ፡ የገዛ ፡ ሰው ፡ ለመጕሰት ፡ ወይም ፡ ለመመጽወት ፡ ይጽና ። ድንገት ፡ የሚገዛውን ፡ እጥቶ ፡ ቢደኸይ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፩ሺ፩፻፩ የራሱ ፡ ያልሆነውን ፡ ቦታ ፡ የሸጠ ፡ ሰው ፡ የገዛትም ፡ ሰው ፡ በውስጧ ፡ ግንብ ፡ ቢሠራ ፡ ምርጫ ፡ መጀመሪያ ፡ ለገዛት ፡ ይሁን ። የዋጋውን ፡ ልክ ፡ ከሸፋጩ ፡ (ከሌባው) ፡ ሊቀበል ፡ ቢወድ ፡ ወይም ፡ የዋጋውን ፡ ልክ ፡ ከገዥ ፡ ሊቀበል ፡ ቢወድ ፡ በቦታው ፡ ውስጥ ፡ ከመሠራቷ ፡ አስቀድሞ ፡ ከዋጋዋ ፡ በኋላ ፡ የተገኘው ፡ በዋጋዋ ፡ ልክ ፡ ለእርሱ ፡ ይሁን ። ለገዥም ፡ ይህን ፡ ቢወድ ፡ ወይም ፡ ከአርጅናው ፡ ያደሰውን ፡ ሊያፈርስ ፡ ቢወድ ፡ ሊመርጥ ፡ ይገባዋል ። መጀመሪያውን ፡ ዋጋ ፡ ከሌባው ፡ ይውሰድ ።

፩ሺ፩፻፪ ሕግ ፡ ግን ፡ የሌቦችን ፡ ገንዘብ ፡ ይገዛ ፡ ዘንድ ፡ በውስጡ ፡ የለም ። ትእዛዝ ፡ ያጻፉለት ፡ ሰውም ፡ ከድኃ ፡ አደጎች ፡ ገንዘብ ፡ ምንምን ፡ ሊገዛ ፡ አይገባውም ። ለመጋቢም ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ ይገባዋል ። ከሹማምት ፡ ወገን ፡ ለማንም ፡ በላዩ ፡ ከተሾመበት ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ከሹመቱ ፡ በታች ፡ ካለ ፡ ሰው ፡ ከሚንቀሳቀሱ ፡ ወይም ፡ ከማይንቀሳቀሱ ፡ በመካከለኛ ፡ ሰው ፡ እጅም ፡ ቢሆን ፡ በራሱም ፡ ቢሆን ፡ በዋጋው ፡ ልክና ፡ በሻጭ ፡ ፈቃድ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ምንም ሊገዛ ፡ አይገባውም ። ያለዚህ ፡ ቢያደርግ ፡ የገዛውን ፡ ከእርሱ ፡ ይውሰዱ ። ዋጋውም ፡ አይመለሰለት ። ነገር ፡ ግን ፡ ሁሉንተናዉን ፡ ለማሳመር ይለይ ።

፩ሺ፩፻፫ ፈራሽ ፡ በሆነ ፡ ውሳኔ ፡ ቃል ፡ የገዛዉን ፡ ፈጽሞ ፡ መውሰድ ፡ አይገባውም ። ይች ፡ ላም ፡ በምትወልድበት ፡ ጊዜ ፡ ልጅዋም ፡ በምትወልድበት ፡ ጊዜ ፡ የተወለደውን ፡ እነሆ ፡ እሸጥልሃለሁ ፡ እንደሚል ፡ ያለ ፡ ነው ። ወይም ፡ ባሪያህን ፡ በኻያ ፡ ብር ፡ ልትሸጥልኝ ፡ በውሳኔ ፡ ደንብ ፡ ይህን ፡ ቦታ ፡ በሃምሳ ፡ ሸጥሁልህ ፡ እንደሚል ፡ ነው ። ወይም ፡ ይህን ፡ ባሪያ ፡ እጅ ፡ በእጅ ፡ በአሥር ፡ ወይም ፡ ቀጠሮ ፡ በመስጠት ፡ በኻያ ፡ ሸጬልሃለሁ ፡ እንደሚል ፡ ነው ።

አንቀጽ ፡ ፴፫ ።

፩ሺ፩፻፬ ምዕራፍ ፡ ኃምስ ። በእንተ ፡ ዘይጸላእ ፡ ገቢሮቱ ፡ ወዘየሐርሙ ፡ በውስተ ፡ ተሣይጦ ። ጽሉእ ፡ ውእቱ ፡ ዘይከውን ፡ ለእሕሥዎ ፡ ፈሊጥ ፡ ማእከለ ፡ እመት ፡ ወወልዳ ፡ ወፈድፋደ ፡ እምቅድመ ፡ ያብጽሕ ፡ መጠነ ፡ እካል ፡ ወፈሊጠ ፡ ገብር ፡ ወእኁሁ ፡ ወፈሊጠ ፡ ገብር ፡ ወብእሲቱ ፡ ወወልዱ ። ወከማሁ ፡ ሠይጠ ፡ ዘተመስለ ፡ በግዕዘ ፡ ሀገር ፡ ለዘኢተመስለ ፡ በግዕዘ ፡ ሀገር ፡ ዘእንበለ ፡ በሥምረተ ፡ ሥዩጥ ። ወጽሉእ ፡ ውእቱ ፡ ዘይብሎ ፡ ለዘተሣየጠ ፡ ምንተኒ ፡ በሥርዓተ ፡ ውሳኔ ፡ ዘኀርየት ፡ ሠዐር ፡ ሤጠከ ፡ ወአነ ፡ እሠይጥ ፡ ለከ ፡ በዘይውሕድ ፡ እው ፡ በከመ ፡ ሤጠ ፡ ዚእሁ ፡ ወንዋየ ፡ ዚአየ ፡ ይኄይስ ፡ ወጽሉእ ፡ ውእቱ ፡ ለእመ ፡ ወፅአ ፡ ብእሲ ፡ ከመ ፡ ይሣጥ ፡ ዘይከውኖ ፡ ለበቍዔት ፡ ወይብሎ ፡ ካልኡ ፡ ኢትሣጥ ፡ እስከ ፡ አነ ፡ እሠይጥ ፡ ለከ ፡ በበንስቲት ፡ በብዙኅ ፡ ሤጥ ። ወጽሉእ ፡ ውእቱ ፡ ተሣይጦ ፡ በመዋዕለ ፡ እሑዳት ፡ ወበበዓላተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወበበዓላተ ፡ እግዝእትነ ፡ ማርያም ። ወለዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ እምከመ ፡ ተሰነአወ ፡ ላዕሌሁ ፡ ተፈጸመ ፡ ተሣይጦ

፩ሺ፩፻፭ ወጽሉእ ፡ ውእቱ ፡ ለእመ ፡ ረከበ ፡ ዘቀደመ ፡ ቍማሰ ፡ ቀራቢብ ። ወተዘያነወ ፡ በእንተ ፡ ሢጡ ፡ ወተሣየጠ ፡ ኪያሁ ፡ እው ፡ እምጽእ ፡ ዘይሣየጥ ፡ ሎቱ ፡ በዘየሐጽጽ ፡ እምሢጡ ፡ ዘውእቱ ፡ ጊዜ ፡ በመካን ፡ ዘመጽአ ፡ ከመ ፡ ይሢጥ ፡ በውስቴቱ ። ወእምከመ ፡ ተዓውቆ ፡ ለሠያጢ ፡ በውእቱ ፡ ጊዜ ፡ ዘፈቀደ ፡ ይኅረይ ፡ ወይሠዐር ፡ ተውሳከ ፡ ዘነገረ ፡ ሤጥ ፡ እው ፡ ለእመ ፡ ተሣየጠ ፡ በ፲ቱ ፡ ወሤጠ ፡ ላዕለ ፡ ሱታፌሁ ። እመኒ ፡ ገብሩ ፡ እው ፡ ዓርከ ፡ ዚእሁ ፡ በ፳ ፡ እው ፡ በዘይንእስ ፡ ይንግርዎ ፡ ዘንተ ፡ ለተሣያጢ ፡ እው ፡ ያግብእ ፡ ወይሣየጦ ፡ እምኔሆሙ ፡ በወሰኮ ፡ ወይንግሩ ፡ ሢጦ ፡ በውሳኬ ፡ ዘተወሰነ ፡ በጕሕሉት ። ወኵሉ ፡ ዘቦቱ ፡ ምክንያት ፡ ላዕለ ፡ ሢጥ ፡ ጽሉእ ፡ ውእቱ ፡ ወሕሩም ፡ ውእቱ ፡ ሐሳበ ፡ ሤጥ ፡ ወከሊእ ፡ ብዉሕ ፡ ወከሊእ ፡ መፍቅዳት ፡ ከመ ፡ ይትወሰክ ፡ ሤጠ ፡ ዚእሁ ፡ ከመ ፡ ይብዛኅ ፡ ዘከመ ፡ በሊዕ ፡ ወሰትዮ ፡ ወልብስ ፡ ወማኅደር ፡ ወኵሉ ፡ ዘይትፈቀድ ፡ እምተገብሮ ።

፩ሺ፩፻፮ ምዕራፍ ፡ ሳድስ ። ወቃልኒ ፡ ዘቀደመ ፡ ተሰናእ

ስለ ፡ መሸጥና ፡ መግዛት ።

፩ሺ፩፻፬ ፭ኛ ፡ ምዕራፍ ፡ መሠራቱ ፡ ስለሚጠላና ፡ በመገበያየት ፡ ጊዜ ፡ ስለሚከለከሉት ፡ ይናገራል ። ለማሳዘን ፡ የሚሆን ፡ የተጠላ ፡ ነው ። ሴት ፡ ባሪያን ፡ ከልጅዋ ፡ መለየት ፡ ይልቁንም ፡ እካለ ፡ መጠን ፡ ከማድረሱ ፡ አስቀድሞ ፡ ወንድ ፡ ባሪያን ፡ ከወንድሙ ፡ መለየት ፡ ወንድ ፡ ባሪያን ፡ ከሚስቱና ፡ ከልጁ ፡ መለየት ፡ የተጠላ ፡ ነው ። በሀገር ፡ ባህል ፡ (ቋንቋ) ፡ የመሰለውን ፡ በሀገር ፡ ባህል ፡ (ቋንቋ) ፡ ላልመሰለው ፡ በሚሸጠው ፡ ፈቃድ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ መሸጥም ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። በምርጫ ፡ ውሳኔ ፡ ደንብ ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ የገዛውን ፡ ሰው ፡ ዋጋህን ፡ አፍርስ ፡ እኔ ፡ በቀላል ፡ ዋጋ ፡ እሸጥልሃለሁ ። ወይም ፡ እንደዋጋው ፡ የእኔም ፡ ዕቃ ፡ ይሻላል ፡ የሚለው ፡ የተጠላ ፡ ነው ። ሰው ፡ ለጥቅም ፡ የሚሆነውን ፡ ለመሸጥ ፡ ቢወጣ ፡ ሌላውም ፡ እኔ ፡ ጥቂት ፡ ጥቂት ፡ እያልኩ ፡ በብዙ ፡ ዋጋ ፡ እስክሸጥልህ ፡ ድረስ ፡ አትሸጥ ፡ ቢለው ፡ የተጠላ ፡ ነው ። በእሑድ ፡ ቀን ፡ በእግዚአብሔር ፡ በዓላቶችና ፡ በእመቤታችን ፡ ማርያም ፡ በዐላቶች ፡ መገበያየት ፡ የተጠላ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ከተስማማበት ፡ መገበያየቱ ፡ ተፈጸመ ።

፩ሺ፩፻፭ የቀደመ ፡ ጥቅል ፡ ጣቃ ፡ ቢያገኝ ፡ ስለ ፡ ዋጋው ፡ ቢነጋገሩና ፡ እርሱን ፡ ቢገዛው ፡ ወይም ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ሊሸጥ ፡ በመጣበት ፡ ቦታ ፡ ከሚያወጣው ፡ ዋጋ ፡ እዋርዶ ፡ የሚገዛለት ፡ ሰው ፡ (ደላላ) ፡ ቢያመጣ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ለሻጭ ፡ ቢታወቀው ፡ የወደደውን ፡ ይምረጥ ። የዋጋው ፡ ንግግር ፡ ጭማሪ ፡ ይፈርሳል ። ወይም ፡ በአሥር ፡ ቢገዛው ፡ ለጓደኛው ፡ ባሪያው ፡ ወይም ፡ ወዳጁ ፡ ቢሆን ፡ በኻያ ፡ ወይም ፡ በሚያንስ ፡ ቢሸጥ ፡ ለገዥ ፡ ይህን ፡ ይንገሩት ። ወይም ፡ መልሶ ፡ ከእነርሱ ፡ በጭማሪ ፡ ይግዛው ። በተንኮል ፡ በጭማሪ ፡ የተወሰነውን ፡ ዋጋ ፡ ይንገሩ ። በዋጋ ፡ ላይ ፡ ምክንያት ፡ ያለበት ፡ ሁሉ ፡ የተጠላ ፡ ነው ። ዋጋን ፡ መገመት ፡ የሚገባውንም ፡ መከልከል ፡ ዋጋው ፡ ይጨመርና ፡ ይበዛ ፡ ዘንድ ፡ የሚሻውን ፡ መከልከልም ፡ የተከለከለ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ እንደመብል ፡ እንደመጠጥ ፡ እንደ ፡ ልብስ ፡ እንደማደሪያ ፡ ከሥራ ፡ ወገንም ፡ እንደሚያሻው ፡ ሁሉ ፡ ያለ ፡ ነው ።

፩ሺ፩፻፮ ፮ኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ስምምነቱ ፡ የቀደመ ፡ ነገር ፡ የተገባ

ምተ ፡ ድልው ፡ ውእቱ ፡ ወይጸላእ ፡ እሕጽጸ ፡ ሢጥ ፡ እው ፡ እብዝኖቱ ፡ እምቃል ፡ ዘቀዳሚ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ነውር ፡ በሥዩጥ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይሢጥዎ ፡ በዘይውሕድ ፡ እምሤጡ ፡ ዘከመ ፡ ተማይጦ ፡ ካልእ ። ወለእመ ፡ ተኀጥአ ፡ መንፈቁ ፡ ለዘይሠይጥዎ ፡ ይደሉ ፡ ተማይጦቱ ፡ በውሑድ ፡ ለዘተርፈ ፡ በመጠነ ፡ ሤጡ ። ወለእመ ፡ ተነሥአ ፡ ዘለንጉሡ ፡ ተፀርዐት ፡ ተማይጦ ፡ ወለእመ ፡ ኢተሐጕለ ፡ ዘለንጉሡ ፡ ሢጥ ፡ ኢትፀራዕ ። ወለእመ ፡ ተረክበ ፡ በውስተ ፡ ማኅደር ፡ ዘተሠይጠ ፡ ወርቅ ፡ ወብሩር ፡ ዘተደፍነ ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ ወተሠወረ ፡ እምእግዚእ ፡ ወነበረ ፡ ውስተ ፡ መካኑ ፡ ያግብእ ፡ ውእቱ ፡ ንዋየ ፡ ኀበ ፡ መላኪሁ ፡ ዘቀዳሚ ።

፩ሺ.፩፻፺፯ ምዕራፍ ፡ ሳብዕ ፡ በእንተ ፡ ድርጎ ፡ ዘይዳርግዎ ፡ ኢትከውን ፡ እማኔ ፡ ተዳርጎ ፡ ዘእንበለ ፡ በሥምረተ ፡ ዳራጊ ፡ ወተዳራጊ ፡ ወኢይትፌቀድ ፡ ኀበ ፡ ሥምረቱ ፡ ለዘድሩግ ፡ ላዕሌሁ ፡ ለእመ ፡ ኢኮነ ፡ ሎቱ ፡ ዝንቱ ፡ በሥምረቱ ። ወፍጻሜሁ ፡ ያመጽእ ፡ ባእስ ፡ ተዳራጊ ፡ ኀቤሁ ፡ እስመ ፡ ተዳርጎሰ ፡ ሠናይ ፡ ውእቱ ፡ በተሰናእዎ ፡ ወፈቃድ ፡ መጠነ ፡ ዘዳረገ ፡ ቦቱ ። ወኢይወስን ፡ ዘይዳረግ ፡ ሥምረተ ፡ ዘይዳርጎ ፡ ለእመ ፡ እልቦቱ ፡ በኀቤሁ ፡ ወእመኒ ፡ ተሰነአወ ፡ ዳራጊ ፡ ሥምረተ ፡ ዘይዳርጎ ፡ ይትፌጸም ፡ በሥምረቱ ፡ በእምጣነ ፡ ዘሀለወ ፡ ንዋዩ ፡ ኀቤሁ ። እው ፡ ዘሠምሮ ፡ እው ፡ ተሀውቀ ፡ ዘድሩግ ፡ ላዕሌሁ ፡ ዘፍጡን ፡ እው ፡ በዕድሜ ፡ ትከውን ፡ እማኔ ፡ ዳርጎቱ ፡ ከማሁ ፡ ወለእመ ፡ ተፈጸመት ፡ ዳርጎት ፡ በሥምረት ፡ ዘኮነ ፡ ንዋየ ፡ ወዕእት ፡ ዳርጎት ፡ እምርእስ ፡ ዳራጊ ፡ ኀበ ፡ ርእስ ፡ ዘተዳራጊ ፡ ላዕሌሁ ። ወለእመ ፡ ዳረገ ፡ ሠያጢ ፡ ላዕለ ፡ ተሣያጢ ፡ ብእሲ ፡ በንዋይ ፡ ወለእመ ፡ አግብአ ፡ ዘተሣየጠ ፡ ላዕለ ፡ ሠያጢ ፡ ገብአ ፡ ንዋየ ፡ ድሩግ ፡ ኀበ ፡ ሠያጢ ፡ ወለእመ ፡ ሤጠ ፡ እምኔሁ ፡ እምሤጥ ፡ በእንተ ፡ ነውር ፡ ከመ ፡ ኢየሀሉ ፡ ኀበ ፡ ተሣያጢ ፡ መጠነ ፡ ንዋይ ፡ ድሩግ ፡ ገብአት ፡ ፍጻሜ ፡ ላዕለ ፡ ሠያጢ ።



ነው ። ዋጋን ፡ ማጕደል ፡ ወይም ፡ ከመጀመሪያው ፡ ቃል ፡ ማብዛት ፡ የተጠላ ፡ ነው ። በሚሸጠው ፡ ነውር ፡ ቢገኝበት ፡ ከዋጋው ፡ በሚያንስ ፡ ሊሸጡት ፡ ይገባል ። ይኸውም ፡ ሌላ ፡ እንደመግዛት ፡ ነው ። ለሚሸጡት ፡ ነገር ፡ እኩሌታው ፡ ቢጠፋ ፡ የቀረውን ፡ በዋጋው ፡ ልክ ፡ በቅናሽ ፡ ዋጋ ፡ ሊገዙት ፡ ይገባል ። መላው ፡ ቢጠፋ ፡ ግን ፡ መገበያየት ፡ ይቀራል ። መላው ፡ ካልጠፋ ፡ ዋጋ ፡ እይቀርም ። በተሸጠ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በጕድጓድ ፡ የተቀበረ ፡ ከጌታውም ፡ የተሰወረና ፡ በቦታዉ ፡ የተቀመጠ ፡ ወርቅ ፡ ብር ፡ ቢገኝ ፡ ያ ፡ ገንዘብ ፡ ወደቀደመ ፡ ጌታዉ ፡ ይመለስ ።

፩ሺ.፩፻፺፯ ፯ኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ስለሚዳርጉት ፡ ድርጎ ፡ ይናገራል ።

በዳራጊና ፡ በተዳራጊ ፡ ፈቃድ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ መደራረግ ፡ እውነተኛ ፡ አትሆንም ። ይህ ፡ በፈቃዱ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የተዳረገበት ፡ ሰው ፡ ፈቃድ ፡ አያሻም ። መጨረሻው ፡ ግን ፡ ተዳራጊ ጠብን ፡ ወደእርሱ ፡ ያመጣል ። በዳረገበት ፡ ልክ ፡ በስምምነትና ፡ በፈቃድ ፡ ድርጎ ፡ ያማረ ፡ ነውና ። ተዳራጊ ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ከሌለው ፡ የዳራጊውን ፡ ፈቃድ ፡ አይወስን ። ዳራጊ ፡ የተዳራጊን ፡ ፈቃድ ፡ ቢወድ ፡ ገንዘቡ ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ እንደመኖሩ ፡ መጠን ፡ በፈቃዱ ፡ ወይም ፡ በወደደው ፡ ይፈጸማል ። ወይም ፡ የዳረጉት ፡ ሰው ፡ በፍጥነት ፡ ወይም ፡ በቀጠሮ ፡ ቢታወቅ ፡ ድርጎ ፡ እንደዚሁ ፡ እውነተኛ ፡ ትሆናለች ። ገንዘብ ፡ የሆነ ፡ ድርጎ ፡ በፈቃድ ፡ ቢፈጸም ፡ ድርጎ ፡ ከዳራጊው ፡ ራስ ፡ ወደተዳራጊ ፡ ራስ ፡ ወጣ ። ሻጭ ፡ ከገዥ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ገንዘብ ፡ ቢዳርግ ፡ የገዛም ፡ ለሻጭ ፡ ቢመልስ ፡ የድርጎኛው ፡ ገንዘብ ፡ ወደ ሻጭ ፡ ይመለሳል ። በተዳረገው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ በገዥ ፡ ዘንድ ፡ እንዳይኖር ፡ ስለ ፡ ነውር ፡ (በነውር ፡ ምክንያት) ፡ ከዋጋው ፡ ከእርሱ ፡ ቢመልስም ፡ ፍጻሜ ፡ ወደሻጭ ፡ ተመለሰች ።

# አንቀጽ ፴ወ፬ቱ ።

## በእንተ ፡ ተሳትፎ ።

፩ሺ.፩፻፺፰ እምእብጥሊስ ፡ ዘ፲ወ፱ቱ ፡ ወ፰ ፡ ወካልእኒ ። ተሳትፎስ ፡ ትከውን ፡ በቃል ፡ ወበገቢር ፡ ወበተልእኮ ፡ ማእከለ ፡ ኵሉ ፡ ዘይደሉ ፡ ሥርዓቱ ። ወትከውን ፡ እማነ ፡ በእንተ ፡ ነጊድ ፡ ወእስተዋጽኦ ፡ ወበእንተ ፡ ኵሉ ፡ ንዋይ ፡ ዘየኀሥሡ ፡ ረባኀ ፡ ዚአሁ ፡ ወማእከለ ፡ እለ ፡ ኢይትኤረዩ ፡ በብዕል ፡ እስመ ፡ ነዳይ ፡ እምኔሆሙ ፡ ነዋ ፡ ይፌጽም ፡ መፍቅዶ ፡ ዘነጥአ ፡ እምንዋይ ፡ በተውሳካት ፡ እንዘ ፡ ያስተሐምም ፡ ውስተ ፡ ዕቅበት ። ወለእመ ፡ ኮነት ፡ ተሳትፎቶሙ ፡ በመልእክት ፡ ዘኢተዘከረ ፡ ኀበ ፡ እይኒ ፡ ግብር ፡ ከዊኖታ ፡ ይእቲ ፡ ትከውን ፡ ላዕለ ፡ ንዋይ ፡ ዘሀለወ ፡ ዘይጠረይ ፡ እምግብር ፡ ዘእንበለ ፡ ርስት ፡ ወሀብት ፡ ወትእዛዛት ።

፩ሺ.፩፻፺፱ ወለእመ ፡ ኮነት ፡ ተሰናእዎ ፡ ማእከለ ፡ ሱቱፋን ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ዘይበጽሖሙ ፡ እምርስቶሙ ፡ ለተሳትፎ ፡ ማእከሎሙ ፡ ኢያብኡኬ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ በዘተእዘዘ ፡ ሎሙ ። ወለእመ ፡ ኮነት ፡ ተሰናእዎቶሙ ፡ ከመ ፡ ኢይሥዐሩ ፡ ተሳትፎቶሙ ፡ እስከ ፡ ጊዜ ፡ እሙር ፡ ዕዳ ፡ ይደልዎ ፡ ለዘይሥዕሩ ፡ እቅዲሙ ፡ ዘእንበለ ፡ በምክንያት ፡ ዘይደሉ ፡ እስከ ፡ ኮነ ፡ ሥርዓተ ፡ ተሰናእዎቶሙ ፡ ዘኢተፈጸመ ፡ እው ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ሱቱፍ ፡ ዐብደ ፡ ወዘራዊ ፡ ንዋይ ፡ ወዘይከውን ፡ እምሀኬቱ ፡ እው ፡ እምኮሕሉቱ ፡ ለተሳታፊሁ ፡ ይደልዎ ፡ ዕዳ ፡ ለባሕቲቱ ።

፩ሺ.፪፻ ወዘተሰርቀስ ፡ ወተዳደቆ ፡ ጥፍአት ፡ ወእበተዋዕኦ ፡ መፍቅዳት ፡ ዘኢይከውን ፡ ድልወ ፡ ለ፩ዱ ፡ ባሕቲቱ ፡ እምውሉድ ፡ ወዘመድ ፡ ወተለቅሖ ፡ ዝንቱስ ፡ ይደልዎሙ ፡ ለክልኤሆሙ ። ወከማሁ ፡ ተንኮሎተ ፡ ንዋይ ፡ ወረባኁ ፡ ወእልቦ ፡ ሱታፌ ፡ ማእከለ ፡ ፩ዱ ፡ ወካልኡ ፡ በዘእጥረዮ ፡ በእፍኢ ፡ እምንዋየ ፡ ተሳትፎ ። ወለእመ ፡ ጠፍአ ፡ ንዋየ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ በባሕቲቱ ፡ እምድኅረ ፡ ተሳትፎ ፡ ኢይደልዎ ፡ በባሕቲቱ ፡ እላ ፡ ለ፪ሆሙ ። ወለእመኒ ፡ ተረክበ ፡ ኅጥ ፡ እው ፡ ተዓበዐ ፡ እንተ ፡ እምድኅረ ፡ ውፍየት ፡ ለ፩ዱ ፡ ወኅኮልኒ ፡ ወረባኅኒ ፡ ለ፪ሆሙ ። ወለእመ ፡ ተማየጠ ፡ ሱቱፍ ፡ በንዋይ ፡ ፍሉጥ ፡

# አንቀጽ ፡ ፴፬ ።

## ስለሽርክና ፡ ይናገራል ።

፩ሺ.፩፻፺፰ ከእብጥሊስ ፡ ፲፱ ፡ ፰ ። ከሁለተኛውም ፡ የተገኘ ፡ ነው ። ሽርክና ፡ ግን ፡ በቃል ፡ በሥራ ፡ በማገልገል ፡ ሥርዓቱ ፡ በሚገባ ፡ ሁሉ ፡ መካከል ፡ ትሆናለች ። ስለ ፡ መነገድና ፡ በለመዋጮ፡ ትርፉንም ፡ በለሚፈልጉት ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ በሀብት ፡ በማይተካከሉ ፡ መካከልም ፡ እውነተኛ ፡ ትሆናለች ። ከእነርሱ ፡ ወገን ፡ በመጠበቅ ፡ እየተጋ ፡ ከገንዘብ ፡ ውበጥ ፡ ያጣ ፡ ድኃ ፡ በትርፉ ፡ እነሆ ፡ መፍቅዱን ፡ ይፈጽማልና ። የሽርክናቸው ፡ ሁኔታዋ ፡ በማናቸውም ፡ ሥራ ፡ ያልተነገረ ፡ በመልእክት ፡ ብትሆን ፡ ከሥራ ፡ ይገኝ ፡ ዘንድ ፡ ባለው ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ እርሷ ፡ ትጸናለች ፡ (ትሆናለች) ፡ ከርስትና ፡ ከሀብት ፡ ካዘዙትም ፡ በቀር ።

፩ሺ.፩፻፺፱ ከርስታቸውም ፡ የሚደርሳቸው ፡ ገንዘብ ፡ በመካከላቸው ፡ ሳለው ፡ በምምንት ፡ እንዲሆን ፡ በሽርኮች ፡ መካከል ፡ ስምምነት ፡ ቢሆን ፡ የታዘዙላቸውን ፡ ከዚህ ፡ ውስጥ ፡ እያግቡ ። በምምነታቸው ፡ እስከታወቀ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ሽርክናቸው ፡ እንዳይፈርስ ፡ ቢሆን ፡ የሚገባ ፡ ምክንያት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አስቀድሞ ፡ ለሻራት ፡ ሰው ፡ ዕዳ ፡ ይገባዋል ። የበምምነታቸው ፡ ደንብ ፡ ያልተፈጸመ ፡ ሁኗልና ። ወይም ፡ ሽሪኩ፡ ሰነፍና ፡ ገንዘብ ፡ የሚበትን ፡ ከስንፍናው ፡ ወይም ፡ ከሽሪኩ ፡ ተንኮል ፡ የተነሣ ፡ ቢሆን ፡ ለብቻው ፡ ዕዳ ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ.፪፻ የተሠረቀ ፡ ጥፋትም ፡ ያገኘው ፡ ለግዳጅም ፡ የተወጣጣ ፡ ገንዘብ ፡ ግን ፡ ከልጅ ፡ ከዘመድ ፡ ከብድር ፡ የተነሣ ፡ ለአንዱ ፡ ብቻ ፡ ሊሆን ፡ አይገባም ። ይህስ ፡ ለ፪ቱም ፡ ይገባቸዋል ። የገንዘቡ ፡ ኪሣራና ፡ ትርፍም ፡ እንደዚሁ ነው ። ከሽርክናው ፡ ገንዘብ ፡ ውጭ ፡ ካገኙት ገንዘብ፡ በአንደኛውና ፡ በሁለተኛው ፡ መካከል ፡ ሽርክና ፡ የለም ። ከሽርክና ፡ በኋላ ፡ ከእነርሱ ፡ የአንዱ ፡ ገንዘብ ፡ ብቻውን ፡ ቢጠፋ ፡ ለሁለቱም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለአንዱ ፡ ብቻ ፡ አይገባውም ። ለአንዱ ፡ ከመሰጠቱ ፡ በኋላ ፡ የምትሆን ፡ ዋጋና ፡ ኪራይ ፡ ቢገኝ ፡ ኪሣራም ፡ ትርፍም ፡ ለሁለቱ ፡ ነው ። ሽሪኩ ፡ ገንዘቡ ፡ በሆነ ፡ በተ

አንቀጽ ፡ ፴፩ ።

ዘኮነ ፡ ንዋር ፡ አው ፡ ንዋየ ፡ ሴታፌሁ ፡ ወረ ባኅ ፡ ወኅጕሉ ፡ ሳዕለ ፡ ማእከል ።

፩ሺ፩፻፲፭ ወለእመ ፡ ሐደሰ ፡ አሐዱ ፡ እምሴ-ተፋኑ ፡ ቤተ ፡ ዘይሳተፉ ፡ ኪያሁ ፡ ፈረሆ ፡ ከመ ፡ ኢይማስን ፡ አው ፡ በተሰናእዎ ፡ ሴታፌሁ ፡ ይትኀሠሥ ፡ እስከ ፬ቱ ፡ አውራኅ ፡ በዘእስተዋፅኦ ፡ እምንዋዩ ። ወእምከመ ፡ ተፈጸመት ፡ ዛቲ ፡ ዕድሜ ፡ ወተኀሥሥ ፡ ወኢወሀበ ፡ ዘይደልዎ ፡ ይኩን ፡ በዘ ነረየ ፡ እስመ ፡ ለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ይንበር ፡ በኀ ሠሣሁ ። ወለእመ ፡ ኢፈቀደ ፡ ይንሥአ ፡ ለቤት ፡ እምድኅረ ፡ አመሮ ፡ ለመኰንን ፡ ዘው እቱ ፡ ይሬሲ ፡ ሎቱ ፡ ክፍለ ፡ ዘይረክቦ ፡ ለሱ ቱፍ ፡ በአምጣነ ፡ ዘይደልዎ ፡ እምነ ፡ ዘእስተዋ ፅኦ ፡ እስመ ፡ ሕግ ፡ ያገብእ ፡ ምልክና ፡ ማኅ ደር ፡ ለዘሐነጸ ።

፩ሺ፩፻፲፮ ወልቃሕያትሰ ፡ ዘተሳትፎ ፡ ይፍድዩ ፡ እም ኑሃ ፡ እምቅድመ ፡ ትሠዐር ። ወተሳትፎሰ ፡ ዘኢ ያንቀለቅል ፡ አልቦ ፡ ለአሐዱ ፡ እምሱቱፋን ፡ ከመ ፡ ያስተዋፅእ ፡ ውስተ ፡ ካልእ ፡ ክፍል ፡ ዘእ ንበለ ፡ በትእዛዘ ፡ ዚአሁ ፡ አው ፡ ለመፍቅድ ፡ ዘክሡት ፡ በትእዛዘ ፡ መኰንን ። ወዘእንበለ ፡ ዝንቱሰ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ትኩን ፡ ተሳትፎ ፡ ሳዕለ ፡ ኵሉ ፡ ንዋይ ፡ ወእስተዋፅኦ ፡ ለግብረ ፡ እድ ፡ ወኵሉ ፡ ተገብሮ ፡ ይከውን ፡ ተዓርዮ ፡ አው ፡ አፈድፍዶ ፡ በረባኅ ፡ ውስተ ፡ ሥርወ ፡ ንዋይ ፡ ወዘተግባር ፡ ወዝንቱኒ ፡ በከመ ፡ ኮነ ፡ ተሰናእዎቶሙ ፡ ሳዕሌሁ ።

፩ሺ፩፻፲፫ ወይደሉ ፡ ከመ ፡ ይሳተፍ ፡ ኵሉ ፡ ለለአሐዱ ፡ በኵሉ ፡ ንዋዩ ፡ ወበአሐዱኒ ፡ እምንዋዩ ። ወኢይ ደሉ ፡ ከመ ፡ ይቁም ፡ ሱቱፍ ፡ ሀየንተ ፡ ሌታ ፌሁ ፡ በንዋይ ፡ ዘዚአሁ ፡ ዘእንበለ ፡ በመባ ሕቱ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ተሰናእዎ ፡ ከመ ፡ ይሥ ራዕ ፡ ውስተ ፡ ንዋየ ፡ ተሳትፎ ፡ ዘእንበለ ፡ አሐዱ ፡ እሙር ፡ ዘኢይደሉ ፡ ለካልእ ፡ ከመ ፡ ይሥራዕ ፡ ውስቴቱ ፡ ዘእንበለ ፡ በመባሕቱ ።

፩ሺ፩፻፲፬ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ተሰናእዎ ፡ ሳዕለ ፡ ፪ቱ ፡ እው ፡ በ፫ቱ ፡ እው ፡ በዘይበዝኅ ፡ ከመ ፡ ይሥራዕ ፡ ውስቴቱ ፡ ይደሉ ። ወለሱቱፍ ፡ ኢይደልዎ ፡ በዘይሣየጥ ፡ ወይሠይጥ ፡ ወበዘይስእሎ ፡ እም ኅጕለ ፡ ንዋይ ፡ አው ፡ በእጥፍአቱ ፡ ወበዘይለ ክዮ ፡ እምተንኀልዎ ፡ ዳእሙ ፡ በጥያቄ ፡ ስምዕ ።

ስለ ፡ ሽርክና ።

ለየ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ በሽሪኩ ፡ ገንዘብ ፡ ቢገዛ ኪሣራውና ፡ ትርፋም ፡ በመካከላቸው ፡ ነው ።

፩ሺ፩፻፲፭ ከተሻረኩት ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ የጋራ ፡ ቤታ ቸው ፡ እንዳያፈርስ ፡ ፈርቶ ፡ ወይም ፡ በሽሪኩ ፡ ስምምነት ፡ ቢያድስ ፡ እስከ ፡ አራት ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ ያወጣጣዉን ፡ ገንዘብ ፡ ይጠይቀው ። ይችም ፡ ቀጠሮ ፡ ብትፈጸም ፡ ቢፈላለገውም ፡ የሚገባውንም ፡ ባይሰጠው ፡ እሠሪዉ ፡ እንደ መረጠ ፡ ይሁን ። ቢወድ ፡ በመፈሳለት ፡ ይቆይ። ባይወድ ፡ ግን ፡ ለዳኛ ፡ ካመለከተ ፡ በኋላ ፡ ቤቱን ፡ ይውሰድ ። ይኸውም ፡ ካወጣው ፡ ገን ዘብ ፡ የሚገባውን ፡ ያዘል ፡ ለሽሪኩ ፡ የሚደርስ ውን ፡ ክፍያ ፡ የሚያደርግ ፡ ነው ። ሕግ ፡ የቤ ቱን ፡ እጅነት ፡ (ሥልጣን) ፡ ለሠሪዉ ፡ ይፈቅድ ለታልና ።

፩ሺ፩፻፲፮ የሽርክና ፡ ብድርን ፡ ግን ፡ ከመሻሯ ፡ አስቀ ድሞ ፡ ከእርሷ ፡ ይክፈሉ ። የማይፈርስ ፡ ሽር ክና ፡ ግን ፡ ከሽሪኮቹ ፡ ለአንዱ ፡ ለሌላ ፡ ክፍል ፡ ሊያወጣው ፡ አይገባውም ። በእርሱ ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ በዳኛ ፡ ትእዛዝ ፡ ለታወቀ ፡ መፍቅድ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ያለዚህ ፡ ግን ፡ በገንዘብ ፡ ሁሉ፡ ሽርክና ፡ መግባት ፡ ለተግባረ ፡ እድም ፡ ማወ ጣጣት ፡ ይገባል ። ሥራ ፡ ሁሉ ፡ በገንዘቡና ፡ በሥራዉ ፡ ዓይነት ፡ በትክክል ፡ ወይም ፡ ትር ፍን ፡ በማብዛት ፡ ይሆናል ። ይኸውም ፡ በእ ርሱ ፡ ላይ ፡ እንደተስማሙ ፡ ነው ።

፩ሺ፩፻፲፫ ሁሉም ፡ እያንዳንዱ ፡ በገንዘቡ ፡ ሁሉ ፡ ወይም፡ ከገንዘቡ ፡ በአንዱ ፡ ሽርክና ፡ ሊገባ ፡ ይገባል ። ሽርክና ፡ ያለው ፡ ያለፈቃድ ፡ ለሽሪኩ ፡ ሊቆም ፡ አይገባም ። በሽክ፡ናው ፡ ገንዘብ ፡ ያለአንደ ኛው ፡ ሊሠራ ፡ ስምምነት ፡ ቢኖር ፡ ያለፈቃዱ ፡ በገንዘቡ ፡ ሊሠራበት ፡ እንዳይገባ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

፩ሺ፩፻፲፬ በ፪ ፡ ወይም ፡ በ፫ ፡ ወይም ፡ በሚበዛ ፡ ስምም ነት ፡ ቢደረግ ፡ ሊሠራበት ፡ ይገባል ። ሽሪኩ ፡ በሚገዛውና ፡ በሚሸጠው ፡ በገንዘብ ፡ ጥፋት ፡ ወይም ፡ በማጥፋቱ ፡ በሚከሰውም ፡ ገንዘብ ፡ እርሱንም ፡ ከተንኮልና ፡ ከመሥረቅ ፡ ከስንፍ ናም ፡ የተነሣ ፡ በሚከሱት ፡ ገንዘብ ፡ ሊከፍል ፡ አይገባውም ፡ በምስክር ፡ አስረጅነት ፡ ቢሆን ፡ ነው ፡ እንጂ ።

አንቀጽ ፥ ፴፰ ።

፩ሺ፩፻፲፩ ወለእመ ፥ ሠዐረ ፥ ፩ዱ ፥ እምስቱፋን ፥ ለሱታፌሁ ፥ እምሥርዓት ፥ ዘተፈልጠ ፥ ወይሄሉ ፥ ካልኡኒ ፥ ላዕለ ፥ ሥርዓት ፥ እስከ ፥ ይፈልጦ ፥ ካልኡኒ ። ወለእመ ፥ ሞተ ፥ ፩ዱ ፥ እምኔሆሙ ፥ አው ፥ ዐብደ ፥ አው ፥ ታሕተ ፥ ምግበ ፥ ካልእ ፥ አው ፥ ተፈትሐ ፥ ላዕሌሁ ፥ ፍትሐ ፥ ሞት ፥ ተሠዐረት ፥ ሱታፌ ፥ እምኔሁ ።

፩ሺ፩፻፲፪ ወለእመ ፥ ተፈጸመት ፥ ሰዓቲሃ ፥ ተሳትፎ ፥ አው ፥ በተኀጥአ ፥ ንዋይ ፥ ዘተሰነአዉ ፥ ላዕሌሁ ፥ አው ፥ ኮነት ፥ ተከልአ ፥ በግብር ፥ እምግብሮሙ ፥ ውስቴቱ ። አው ፥ ለእመ ፥ አበዩ ፥ ኵሉ ፥ ለለ፩ዱ ፥ እምስቱፋን ፥ አው ፥ ለእመ ፥ ተኀሠሠ ፥ ፩ዱ ፥ ለካልኡ ፥ በኵሉ ፥ ንዋዩ ፥ በቃለ ሐተታ ፥ አው ፥ በመንበረ ፥ ፍትሕ ፥ አው ፥ ሠርዐ ፥ እምእሉ ፥ ለለ፩ዱ ፥ በአስተራብኖ ፥ ንዋዩ ፥ በባሕቲቱ ፥ ተሠዐረት ፥ ተሳትፎ ።

ስለ ፥ ማስገደድና ፥ ቅሚያ ።

፩ሺ፩፻፲፩ ከሽሪኮች ፥ አንዱ ፥ በመለየት ፥ ሥርዓት ፥ ሽርክናውን ፥ ቢያፈርስ ፥ ሌላውም ፥ ሌላው ፥ እስኪለየው ፥ ድረስ ፥ በሥርዓቱ ፥ ይኖራል ። ከእነርሱ ፥ አንዱ ፥ ቢሞት ፥ ወይም ፥ አእምሮውን ፥ ቢያጣ ፥ ወይም ፥ ከሌላው ፥ አስተዳደር ፥ በታች ፥ ቢሆን ፥ ወይም ፥ የሞት ፥ ፍርድ ፥ ቢፈረድበት ፥ ሽርክናው ፥ ከእርሱ ፥ ዘንድ ፥ ትሻራለች ።

፩ሺ፩፻፲፪ የሽርክናው ፥ ዘመን ፥ ቢፈጸም ፥ ወይም ፥ በተስማሙበት ፥ ገንዘብ ፥ መታጣት ፥ ወይም ፥ በግድ ፥ ከሥራው ፥ መከልከል ፥ ብትሆንበት ፥ ወይም ፥ ከሽሪኮች ፥ እያንዳንዳቸው ፥ ሁሉም ፥ እንቢ ፥ ቢሉ ፥ ወይም ፥ አንዱ ፥ ሌላውን ፥ በገንዘቡ ፥ ሁሉ ፥ በምርመራ ፥ ቃል ፥ ወይም ፥ በፍርድ ፥ ሸንጎ ፥ ቢፈላሰገው ፥ ወይም ፥ ከእነርሱ ፥ እያንዳንዱ ፥ ገንዘቡን ፥ ለብቻው ፥ በማራባት ፥ ቢያከናውን ፥ ሽርክና ፥ ትፈርሳለች ።

## አንቀጽ ፴ወ፱ቱ ።

በእንተ ፥ አገብሮ ፥ ወተኀይሎ ።

፩ሺ፩፻፲፫ አገብሮሰ ፥ ለእመ ፥ ኮነ ፥ ላዕለ ፥ ክሒደ ፥ ሃይማኖት ፥ ወተአመነ ፥ እምሕሊናሁ ፥ ኢይደሉ ፥ ግሙራ ፥ በከመ ፥ ተነግረ ፥ ውስተ ፥ አንቀጸ ፥ ሰማዕት ፥ ወዘይበውእ ፥ ኮንኑ ፥ በእንተ ሃይማኖት ፥ ወለእመ ፥ ተቀትለ ፥ ውእቱኒ ፥ ሰማዕት ። ወለእመ ፥ ይኀንን ፥ እንዘ ፥ ማእምን ፥ ሰምዐ ፥ ክዊኖ ፥ ውእቱ ፥ ዘይሰመይ ፥ ምእመን ፥ ሰምዐ ፥ ወመዓርጉሂ ፥ እምድኅረ ፥ መዓርገ ፥ ሰማዕት ፥ ወቀረቦቱ ፥ ኀቤሁ ፥ በመጠነ ሕማም ፥ ዘፆረ ፥ ወሐለየ ፥ በዐቂሮቱ ።

፩ሺ፩፻፲፬ ወለእመ ፥ ኮነ ፥ አገብሮ ፥ በእንተ ፥ ኀዲገ ፥ ትእዛዝ ፥ አው ፥ በእንተ ፥ ዘይመጽእ ፥ ላዕሌሁ ፥ ለልወት ፥ አው ፥ ቀትል ፥ አው ፥ ዝሙት ፥ ይደሉ ፥ ከመ ፥ ይፁር ፥ ዘኢይትፈረሀ ፥ እምኔሁ ፥ ኀጕለ ፥ ነፍስ ፥ ወኢ ፥ ሙስና ፥ ፩ዱ ፥ እባል ፥ እምአባለ ፥ ሥጋ ።

፩ሺ፩፻፲፭ ወኢይደሉ ፥ ተወክፎ ፥ ዘእንበለ ፥ ትዕግሥት ፥ በዐቂረ ፥ ምንዳቤ ፥ ዘበጽሐ ፥ ወተዓቅቦ ፥ እምኀጕል ፥ ለዘይትከሀሎ ፥ ነሢአ ፥ በቀኖት ፥ ዘይትገፎ ፥ ኪያሁ ፥ ወይደሉ ፥ ከመ ፥ ይኩን ፥

## አንቀጽ ፥ ፴፱ ።

ስለማገበርና ፥ ስለቅሚያ ፥ ይናገራል ።

፩ሺ፩፻፲፫ አገብሮስ ፥ ሃይማኖትን ፥ በመካድ ፥ ላይ ፥ ቢሆን ፥ ከሕሊናውም ፥ ቢያምን ፥ ፈጽሞ ፥ አይገባም ። በአንቀጸ ፥ ሰማዕት ፥ እንደተነገረ (ፍት ፥ ነገ ፥ ፯፻፵፯) ። ስለሃይማኖት ፥ ቅጣትን ፥ የሚቀበል ፥ ቢኖር ፥ ቢሞትም ፥ ሰማዕት ፥ እርሱ ፥ ነው ። እማኒ ፥ ሳለ ፥ ምስክር ፥ ሁኖ ፥ ቢድን ፥ የታመነ ፥ ምስክር ፥ የሚባል ፥ እርሱ ፥ ነው ። መዓርጉም ፥ ከሰማዕት ፥ መዓርግ ፥ ቀጥሎ ፥ ነውወደ ፥ እርሱም ፥ መቅረቡ ፥ በተቀበለውና ፥ ተቀብሎም ፥ ባሰበው ፥ መከራ ፥ ልክ ፥ ነው ።

፩ሺ፩፻፲፬ አገብሮ ፥ ትእዛዝን ፥ ስለማስተው ፥ ወይም ፥ በራሱ ፥ ላይ ፥ ስለሚመጣው ፥ ወንጀል ፥ ወይም ፥ ሞት ፥ ወይም ፥ ዝሙት ፥ ቢሆን ፥ ከእርሱ ፥ የነፍስ ፥ ጥፋትና ፥ ከሥጋ ፥ ሕዋስ ፥ አንዱን ፥ አካል ከማጥፋት ፥ የተነሣ ፥ የማይፈራውን ፥ ሊሸከም ፥ ይገባል ።

፩ሺ፩፻፲፭ የደረሰውን ፥ መከራ ፥ በመቀበል ፥ ጊዜ ፥ ትዕግሥት ፥ ሳያደርግ ፥ መቀበል ፥ አይገባም ። ከጥፋት ፥ መጠበቅም ፥ እርሱን ፥ ተስፋ ፥ የሚያደርገውን ፥ ጥቅም ፥ ማግኘት ፥ ለሚቻለው ፥ ይገ

አንቀጽ ፡ ፴፭ ።

፩ሺ፩፻፲፭ ወለእመ ፡ ሠበሮ ፡ ፩ዱ ፡ እምሱቱፋን ፡ ለሱታፌሁ ፡ እምሥርዓት ፡ ዘተፈልጠ ፡ ወይሄሉ ፡ ካልኡኒ ፡ ላዕለ ፡ ሥርዓት ፡ እስከ ፡ ይፈልጦ ፡ ካልኡኒ ። ወለእመ ፡ ሞተ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ አው ፡ በብየ ፡ አው ፡ ኃሕተ ፡ ምግበ ፡ ካልኡ ፡ አው ፡ ተፈትሐ ፡ ላዕሌሁ ፡ ፍትሐ ፡ ሞት ፡ ተሥዕረት ፡ ሱታፌ ፡ እምኔሆሙ ።

ስለ ፡ ማስገደድና ፡ ቅሚያ ።

፩ሺ፩፻፲፭ ከሽሪኮች ፡ አንዱ ፡ በመስየት ፡ ሥርዓት ፡ ሽርክናውን ፡ ቢያፈርስ ፡ ሌላውም ፡ ሌላው ፡ እስኪለየው ፡ ድረስ ፡ በሥርዓቱ ፡ ይኖራል ። ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ ቢሞት ፡ ወይም ፡ እእምሮውን ፡ ቢያጣ ፡ ወይም ፡ ከሌላው ፡ አስተዳደር ፡ በታች ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ቢፈረድበት ፡ ሽርክናው ፡ ከእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ትሻራለች ።

፩ሺ፩፻፲፮ ወለእመ ፡ ተፈጸመት ፡ ሰዪማ ፡ ተሳትፎ ፡ አው ፡ በተኀጥአ ፡ ንዋይ ፡ ዘተሰነአወ ፡ ላዕሌሁ ፡ አው ፡ ኮነት ፡ ተኀልአ ፡ በግብር ፡ እምግብናሁ ፡ ውስቴቱ ። አው ፡ ለእመ ፡ አበዩ ፡ ኵሉ ፡ ለለ፩ዱ ፡ እምሱቱፋን ፡ አው ፡ ለእመ ፡ ተኀሠሠ ፡ ፩ዱ ፡ ለካልኡ ፡ በኵሉ ፡ ንዋዩ ፡ በቃለ ሐተታ ፡ አው ፡ በመንበረ ፡ ፍትሕ ፡ አው ፡ ሠርዐ ፡ እምእሉ ፡ ለለ፩ዱ ፡ በእስተራብኖ ፡ ንዋዩ ፡ በባሕቲቱ ፡ ተሥዕረት፡ ተሳትፎ ።

፩ሺ፩፻፲፮ የሽርክናው ፡ ዘመን ፡ ቢፈጸም ፡ ወይም ፡ በተስማሙበት ፡ ገንዘብ ፡ መታጣት ፡ ወይም ፡ በግድ ፡ ከሥራው ፡ መከልከል ፡ ብትሆንበት ፡ ወይም ፡ ከሽሪኮች ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ሁሉም ፡ እንቢ ፡ ቢሉ ፡ ወይም ፡ እንዱ ፡ ሌላውን ፡ በገንዘቡ ፡ ሁሉ ፡ በምርመራ ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ በፍርድ ፡ ሸንጎ ፡ ቢፈላለገው ፡ ወይም ፡ ከእነርሱ ፡ እያንዳንዱ ፡ ገንዘቡን ፡ ለብቻው ፡ በማራባት ፡ ቢያከናውን ፡ ሽርክና ፡ ትፈርሳለች ።

አንቀጽ ፡ ፴ወ፮ቱ ።

በእንተ ፡ እገብር ፡ ወተኀይሎ ።

፩ሺ፩፻፲፯ እገብርሰ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ላዕለ ፡ ክሒደ ፡ ሃይማኖት ፡ ወተእመነ ፡ እምሕሊናሁ ፡ ኢይደሉ ፡ ግሙራ ፡ በከመ ፡ ተነግረ ፡ ውስተ ፡ አንቀጸ ፡ ሰማዕት ፡ ወዘይዐውር ፡ ኵነኔ ፡ በእንተ ሃይማኖት ፡ ወለእመ ፡ ተቀትለ ፡ ውእቱኒ ፡ ሰማዕት ። ወለእመ ፡ ይኄነ ፡ እንዘ ፡ ማእምን ፡ ሰምዐ ፡ ከዊኖ ፡ ውእቱ ፡ ዘይሰመይ ፡ ምእመን ፡ ሰምዐ ፡ ወመዓርጊሁ ፡ እምድኅረ ፡ መዓርገ ፡ ሰማዕት ፡ ወቀረቦቱ ፡ ኀቤሁ ፡ በመጠነ ፡ ሕማም ፡ ዘፆረ ፡ ወሐለየ ፡ በዐቂሮቱ ።

፩ሺ፩፻፲፯ እገብርስ ፡ ሃይማኖትን ፡ በመካድ ፡ ላይ ፡ ቢሆን ፡ ከሕሊናውም ፡ ቢያምን ፡ ፈጽሞ ፡ አይገባም ። በአንቀጸ ፡ ሰማዕት ፡ እንደተነገረ (ፍት ፡ ነገ ፡ ፯፻፶፯) ። ስለሃይማኖት ፡ ቅጣትን ፡ የሚቀበል ፡ ቢኖር ፡ ቢሞትም ፡ ሰማዕት ፡ እርሱ ፡ ነው ። እማኒ ፡ ሳለ ፡ ምስክር ፡ ሁኖ ፡ ቢድን ፡ የታመነ ፡ ምስክር ፡ የሚባል ፡ እርሱ ፡ ነው ። መዓርጉም ፡ ከሰማዕት ፡ መዓርግ ፡ ቀጥሎ ፡ ነው ወይ ፡ እርሱም ፡ መቅረቡ ፡ በተቀበለውና ፡ ተቀብሎም ፡ ባሰበው ፡ መከራ ፡ ልክ ፡ ነው ።

፩ሺ፩፻፲፰ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ እገብር ፡ በእንተ ፡ ኀዳገ ፡ ትእዛዝ ፡ አው ፡ በእንተ ፡ ዘይመጽእ ፡ ላዕሌሁ ፡ ሰልጠት ፡ አው ፡ ቀትል ፡ አው ፡ ዝሙት ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይዑር ፡ ዘኢይትፈራዓህ ፡ እምኔሁ ፡ ኀጕለ ፡ ነፍስ ፡ ወኢ ፡ ሙስና ፡ ፩ዱ ፡ አባል ፡ እምአባለ ፡ ሥጋ ።

፩ሺ፩፻፲፰ እገብር ፡ ትእዛዝን ፡ ስለማስተው ፡ ወይም ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ስለሚመጣው ፡ ወንጀል ፡ ወይም ፡ ሞት ፡ ወይም ፡ ዝሙት ፡ ቢሆን ፡ ከእርሱ ፡ የነፍስ ፡ ጥፋትና ፡ ከሥጋ ፡ ሕዋስ ፡ እንዱን ፡ አካል ከማጥፋት ፡ የተነሣ ፡ የማይፈራውን ፡ ሊሸከም ፡ ይገባል ።

፩ሺ፩፻፲፱ ወኢይደሉ ፡ ተወክፎ ፡ ዘእንበለ ፡ ትዕግሥት ፡ በዐዊረ ፡ ምንዳቤ ፡ ዘበጽሐ ፡ ወተዓትቦ ፡ እምነ ፡ ኀጕል ፡ ለዘይትከሀሎ ፡ ነሢአ ፡ በቀኖናት ፡ ዘይሤኔ ፡ ኪያሁ ፡ ወይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡

፩ሺ፩፻፲፱ የደረሰውን ፡ መከራ ፡ በመቀበል ፡ ጊዜ ፡ ትዕግሥት ፡ ሳያደርግ ፡ መቀበል ፡ አይገባም ። ከጥፋት ፡ መጠበቅም ፡ እርሱን ፡ ተስፋ ፡ የሚያደርገውን ፡ ጥቅም ፡ ማግኘት ፡ ለሚቻለው ፡ ይገ

ጽኑዐ ፡ እው ፡ እሡንዮት ፡ ዘእንበለ ፡ ተከል
እት ። ወፀዊርሰ ፡ በመጠን ፡ ሰበያ ፡ ወናእሳ ፡
ለአንብር ፡ አበሳ ፡ ወነቶንኢ ፡ አንብርሰ ፡ ወሰል
ጡቱ ፡ ለእንባሪ ፡ ላዕለ ፡ ዘአንብር ።

፩ሺ፩፻፳ ወለእመ ፡ አንብርዎ ፡ በቀትል ፡ በእንተ ፡
ቀትለ ፡ ብእሲ ፡ ኢይደልዎ ፡ ተመክሮተ ፡
ዝንቱ ፡ ወኢለንቢረ ፡ ዝሙት ፡ ወፈድፋደሰ ፡
በእንተ ፡ አስተዋስቦ ፡ ሕርምት ።

፩ሺ፩፻፳፩ ወለእመ ፡ አንበርዎ ፡ ለብእሲ ፡ በእንተ ፡
ሠይጠ ፡ ንዋዩ ፡ እው ፡ ሳሰለ ፡ ተሣይጦ ፡ ንዋየ፡
ካልእ ፡ እው ፡ ከመ ፡ የዐስብ ፡ ዘይመልክ ፡
እው ፡ ይትዐሰብ ፡ ምልክተ ፡ ካልእ ፡ እው ፡
ከመ ፡ ይእመኖ ፡ ለካልእ ፡ በዘኢኮነ ፡ ውእቱ ፡
በነቢሁ ፡ ወውእቱ ፡ እንከ ፡ ይደልዎ ፡ በን
ርየት ፡ ለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ይፈጽም ፡ ወለእመ ፡
ኢፈቀደ ፡ ይሥዐር ።

፩ሺ፩፻፳፪ ወአንብሮ ፡ ትሕቢት ፡ ለእመ ፡ አዋፍአ ፡
ንብሩ ፡ ዘኮነ ፡ ሎቱ ፡ በጽልእ ፡ ላዕሌሁቱ ፡
ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይፍዲ ፡ ቁመተ ፡ አምሳሊሁ ፡
ዘከማሁ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘጐየ ፡ ይደልዎ ፡
አብጽሖቱ ፡ እው ፡ ይፍዲ ፡ ፍጹሜ ፡ ቁመት ፡
ዘከማሁ ፡ ወለእመ ፡ አብጽሐ ፡ እምድኅረ ፡
ዝንቱ ፡ ይከውኖ ፡ ለዘአንበርዎ ፡ በሣጠ ፡
ንዋዩ ፡ ይኅረይ ፡ እመ ፡ ያገብእ ፡ ዘነሥእ ፡
እው ፡ ይነሥእ ፡ ለንብረ ፡ ዚእሁ ፡ እው ፡ እመ ፡
ይበቍዖ ፡ ይንሣእ ፡ ንብሮ ፡ ወከማሁ ፡ ለእመ ፡
ኮነ ፡ ዘሤጠ ፡ እው ፡ ወዐቦ ፡ ወእምዝ ፡ ገብአ ፡
ኀቤሁ ።

፩ሺ፩፻፳፫ ወለእመኒ ፡ ኮነ ፡ ዘተማየጠ ፡ በአንብሮ ፡ ናሁ፡
አግእዞ ፡ እው ፡ ጕለቶ ፡ እው ፡ መጽወቶ ፡
ኪያሁ ፡ ይለዎ ፡ አግብኦተ ፡ ሤጡ ፡ ዘከማሁ ፡
ወለእመኒ ፡ ኢተክህሎ ፡ ዝንቱ ፡ ይኩን ፡
በከመ ፡ ኀረየ ፡ ዘአንበርዎ ፡ ለእመ ፡ ፈቀደ ፡
ይጽሐፍ ፡ መጽሐፈ ፡ ዕዳ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወይሌ
ብዎ ፡ እስከ ፡ ጊዜ ፡ ይብዕል ፡ ወይሳተፎ ፡ በዝ
ንቱ ፡ ለፈጽሞ ፡ ጽድቅ ። ወእመ ፡ እኮሰ ፡ ይከ
ውን ፡ ሎቱ ፡ መንፈቀ ፡ ምልክና ፡ በእምባነ ፡
አግብኦተ ፡ ሤጥ ፡ ዘከማሁ ። ወለእመ ፡ አስተ
ዋሰቦ ፡ እው ፡ ተዋስቦ ፡ ውእቱ ፡ ኢይሠዐር ፡
ሤጥ ፡ ወይለዎ ፡ ለእንባሪ ፡ ፍጹሜ ፡ ቁመተ ፡
አምሳል ።

፩ሺ፩፻፳፬ ወእመቦ ፡ ዘአንበሮ ፡ ለእግዚእ ፡ አመት ፡



ባል ። ያለ ፡ መከልከል ፡ በጎ ፡ በማድረግ ፡
ፅኑዕ ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ። ቅጣትንና ፡ ፍርድን ፡
መሸከምስ ፡ በማስገደድ ፡ ማነስና ፡ መብዛት ፡
ልክ ፡ ነው ። ማስገደድና ፡ ያስገዳጅ ፡ ወንጀሉ ፡
በአገባሪው ፡ ላይ ፡ ነው ።

፩ሺ፩፻፳ ሰውን ፡ ስለመግደል ፡ በግዳይ ፡ በስልፍ ፡ ጊዜ
ቢያገብሩት ፡ ይህን ፡ መቀበል ፡ አይገባውም ።
ዝሙት ፡ ለመሥራትም ፡ ቢሆን ፡ ይልቁንም ፡
ስለተከለከለችው ፡ ጋብቻ ።

፩ሺ፩፻፳፩ ሰውን ፡ ገንዘቡን ፡ ለመሸጥ ፡ ወይም ፡ የሌላ
ውን ፡ ገንዘብ ፡ ለመግዛት ፡ ወይም ፡ ገንዘቡን ፡
እንዲያከራይ ፡ ወይም ፡ እርሱ ፡ የሌላውን ፡ ገን
ዘብ ፡ እንዲከራይ ፡ ወይም ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡
ባልሆነው ፡ ነገር ፡ ሌላውን ፡ እንዲያምነው ፡
ቢያገብሩት ፡ እንግዲህ ፡ እርሱ ፡ ምርጫ ፡ ይገ
ባዋል ፡ ቢወድ ፡ ይፈጽም ፡ ባይወድ ፡ ይሻር ።

፩ሺ፩፻፳፪ ማገበር ፡ ዋስትና ፡ ነው ። በመጣላት ፡ ለእ
ርሱ ፡ የሆነ ፡ ባሪያ ፡ ቢያጠፋ ፡ እንደርሱ ፡ የመ
ሰለውን ፡ መተካት ፡ ለእርሱ ፡ ይገባል ። የኮበ
ለለ ፡ ቢሆንም ፡ ሊያደርሰው ፡ ወይም ፡ እንደ
ርሱ ፡ ያለ ፡ ፍጹም ፡ ዓይነቱን ፡ ሊከፍል ፡ ይገ
ባዋል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቢያደርሰው ፡ በገንዘቡ ፡
ዋጋ ፡ ሳገበሩት ፡ ሰው ፡ ይሆነዋል ። የወሰደውን
ቢመልስ ፡ ወይም ፡ ባሪያውን ፡ ሊወስደው ፡
ወይም ፡ ከጠቀመው ፡ ባሪያውን ፡ ይወስደው ፡
ዘንድ ፡ ይምረጥ ። የሸጠው ፡ ወይም ፡ እሳልፎ ፡
የሰጠው ፡ ቢሆን ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ወደእርሱ ፡
ቢመለስ ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ።

፩ሺ፩፻፳፫ በማስገደድ ፡ የገዛውን ፡ ባሪያ ፡ ነፃ ፡ ቢያወ
ጣው ፡ ወይም ፡ ቢጐልተው ፡ ወይም ፡ እርሱን ፡
ቢመጸውተው ፡ እንደእርሱ ፡ ያለውን ፡ ዋጋ ፡
ሊመልስ ፡ ይገባዋል ። ይህ ፡ ባይቻለውም ፡ ያገ
በሩት ፡ ሰው ፡ እንደመረጠው ፡ ይሁን ። ቢወ
ድ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ የዕዳ ፡ ደብዳቤ ፡ ይጻፍ ።
ሀብታም ፡ እስኪሆን ፡ ድረስ ፡ ያስተውለው ፡
(ይታገሠው) ፡ በዚህም ፡ ጽድቅን ፡ ለመፈጸም ፡
ይምሰለው ። ይህ ፡ ባይሆን ፡ ግን ፡ እንደ ፡ እርሱ
ያለ ፡ ዋጋ ፡ በመመለሱ ፡ ልክ ፡ የገንዘብነቱ ፡
እኩሌታ ፡ ለእርሱ ፡ ይሆናል ። ቢያጋባው ፡
ወይም ፡ እርሱ ፡ ቢጋባው ፡ ዋጋ ፡ አይሻርም ።
ላገባሪ ፡ መስሉን ፡ መተካት ፡ ተገባው ።

፩ሺ፩፻፳፬ የባሪያዪቱን ፡ ጌታ ፡ ከእርሱ ፡ እስኪገባት ፡

እስከ ፡ ይማየጣ ፡ እምኔሁ ፡ ወእምዝ ፡ አውሰበ፡ ኪያሃ ፡ እው ፡ አስተዋሰባ ፡ ለካልእ ፡ ኢይሠዐር ፡ ሤጦ ፡ ወደለዎ ፡ ለአገባሪ ፡ ፍጹሜ ፡ ቀመተ ፡ አምሳል ። ወለእመ ፡ ሞተት ፡ በኀቤሁ ፡ ዘተማየጣ ፡ ሎቱ ፡ በአገብሮ ፡ ዘእንበለ ፡ ተኀሕልዎ ፡ ወኢንክየት ፡ እመንገሌሁ ፡ እው ፡ ሄድዎ ፡ እምኔሁ ፡ ኢይደልዎ ፡ ዕዳ ፡ በአግብእተ ፡ ሤጡ ።

፩ሺ.፩፻፳፭ ወለእመ ፡ አገበርዎ ፡ ከመ ፡ ያግዕዝ ፡ ገብሮ ፡ እው ፡ ከመ ፡ ይጉልቆ ፡ እው ፡ ይመጽውቆ ፡ ሎቱ ፡ እው ፡ ከመ ፡ ያስተዋስቦ ፡ ይኩን ፡ በከመ ፡ ኀረየ ፡ ውእቱ ፡ ለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ይኅድግ ፡ ዘተሀሰበ ፡ ሎቱ ፡ ወለእመ ፡ ኢፈቀደ ፡ ያግብእ ፡ ለዘአገበርዎ ፡ ሤጠ ፡ ዚአሁ ።

፩ሺ.፩፻፳፮ ወዘተኀየሎስ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ተኀየሊ ፡ ባዕለ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይፍዲ ፡ ፳ተ ፡ ምክዕቢተ ፡ እው ፡ ፬ተ ፡ በከመ ፡ ተዘከረ ፡ በውስተ ፡ አሪት ፡ ይደልዎ ፡ ዕዳ ፡ በዝንቱ ፡ ወለእመ ፡ ኢተክህሎ ፡ ወተክህሎ ፡ ከመ ፡ ይፍዲ ፡ ምክዕቢተ ፡ በከመ ፡ ተነግረ ፡ በእብጥሊስ ፡ ዘ፴ወ፱ቱ ፡ ይደልዎ ፡ ሎቱ ።

፩ሺ.፩፻፳፯ ወእመ ፡ እኮ ፡ ሥርዓት ፡ ትኤዝዝ ፡ ከመ ፡ ያግብኡ ፡ ንዋየ ፡ ዕጉል ፡ እምተዓጋሊ ፡ ዘሰነቃሁ ፡ እው ፡ እምዘ ፡ ተረክበ ፡ በኀቤሁ ፡ ወለእመ ፡ ኢተረክበ ፡ ዓይኑ ፡ ያግብእ ፡ አምሳሊሁ፡ በመጠነ ፡ ሤጡ ። ለእመ ፡ ኀረየ ፡ ዘተበገልዎ ፡ ንዋዮ ፡ ለእመ ፡ ፈቀደ ፡ በእምጣነ ፡ ሤጡ ፡ ለዘ ተበገሉ ፡ ኪያሁ ፡ በጊዜ ፡ ትዕግልቱ ፡ እው ፡ በጊዜ ፡ ዘነሥአ ፡ ኪያሁ ፡ በጊዜ ፡ ተኳንኖ ፡ በእንቲአሁ ፡ እመ ፡ ተክህሎ ፡ እምተዓጋሊ ፡ ይንሣእ ፡ ዋሕስ ፡ እምዘተዓገሎ ፡ በእምጣነ ፡ ፍትሕ ፡ ዘትደሉ ።

፩ሺ.፩፻፳፰ ወለእመ ፡ ተወለጠ ፡ ዓይነ ፡ ዕጉል ፡ በገቢረ ፡ ተዓጋሊ ፡ በከመ ፡ ዓፀደ ፡ ወገብረ ፡ ውስቴታ ፡ ቤተ ፡ እው ፡ ሐጸረ ፡ ሐጸረ፡ ሐዲስ ፡ እመ ፡ ኮነ ፡ በዕፅ ፡ እው ፡ ሐነጸ ፡ መንበረ ፡ ባቲ፡ ትክውን ፡ ሎቱ ፡ ጥሪተ ፡ ወይደልዎ ፡ ዕዳ ፡ እግብእተ ፡ ሤጣ ፡ ዘከማሁ ፡ እምቅድመ ፡ ይወልጣ ።

፩ሺ.፩፻፳፱ወእመኒ ፡ ኮነ ፡ እንስሳ ፡ ወአስብሐ ፡ ኪያሃ ፡ እው ፡ ገብረ ፡ ዘመበር ፡ ግብረ ፡ እድ ፡ ይደልዎ፡ ለዘተበገልዎ ፡ ከመ ፡ ይኅረይ ፡ ለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ይንሣእ ፡ ሤጦ ፡ ዘእምቅድመ ፡ ተሐድሶቱ ፡



ድረስ ፡ ያገበረው ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ከዚህ ፡ በኋላ፡ እርሷን ፡ ቢያገባት ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ቢያጋባት፡ ዋጋ ፡ አይሻርም ። አገባሪውም ፡ መስሉን ፡ መተካት ፡ ተገባው ፡ በግድ ፡ ለእርሱ ፡ የገዛት ፡ ባሪያ ፡ ያለተንኮል ፡ ከርሱ ፡ በሆል ፡ የደረሰባት ጉዳት ፡ ሳይኖር ፡ ወይም ፡ ከእርሱ ፡ ቢቀሙት ፡ ዋጋ ፡ በሚመልስበት ፡ ጊዜ ፡ ዕዳ ፡ አይገባውም።

፩ሺ.፩፻፳፭ ባሪያውን ፡ ነፃ ፡ እንዲያወጣው ፡ ወይም ፡ እንዲጉልተው ፡ ወይም ፡ ለእርሱ ፡ እንዲመጸውተው ፡ ወይም ፡ እንዲያጋባው ፡ ቢያገብሩት ፡ እርሱ ፡ እንደመረጠው ፡ ይሁን ። ቢወድ ፡ ምንደኛ ፡ የሆነበትን ፡ ይተውለት ። ባይወድ ፡ ግን ፡ ያገበሩት ፡ ሰው ፡ ዋጋውን ፡ ይቀበል ።

፩ሺ.፩፻፳፮ የቅሚያስ ፡ ነገር ፡ እንዲህ ፡ ነው ። ቀማኛው ፡ ባለጸጋ ፡ ቢሆን ፡ ፳ ፡ ወይም ፡ ፬ ፡ እጥፍ ፡ እድርጎ ፡ ሊከፍል ፡ ይገባዋል ። በኦሪት ፡ እንደተነገረ ፡ በዚህ ፡ ዕዳ ፡ ይገባዋል ። (ዘፀ ፡ ፳፪ ፡ ፩) ። በእብጥሊስ ፡ በ፴፱ ፡ እንደተነገረ ፡ በእጠፌታ ፡ ሊከፍል ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ.፩፻፳፯ ይህም ፡ ባይሆን ፡ የተቀማውን ፡ ሰው ፡ ገንዘብ ፡ ከቀማኛው ፡ ሁሉን ፡ ወይም ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ከተገኘው ፡ እንዲመልሱ ፡ ሕግ ፡ ታዛለች ። ዓይነቱም ፡ ባይገኝ ፡ በዋጋው ፡ ልክ ፡ መስሉን ፡ ይመልስ ። ገንዘቡን ፡ የቀሙት ፡ ሰው ፡ ቢመርጥ ፡ እርሱን ፡ በቀሙት ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ በተቀማበት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ እርሱን ፡ በወሰደ ፡ ጊዜ ፡ ስለእርሱ ፡ በተቻለው ፡ ሰዓት ፡ ከቀማኛ ፡ በመፈራረድ ፡ ጊዜ ፡ ቢወድ ፡ በምትገባ ፡ ፍርድ ፡ ልክ ፡ ከቀማኛው ፡ ሰው ፡ ዋስ ፡ ይቀበለው ።

፩ሺ.፩፻፳፰ የተቀማው ፡ ገንዘብ ፡ ዓይነት ፡ በቀማኛ ፡ ሥራ ፡ ቢለወጥ ፡ እንደቦታ ፡ ሁኖ ፡ በውስጧ ፡ ቤት ፡ ቢሠራ ፡ ወይም ፡ አዲስ ፡ አጥር ፡ ቢያጥር ፡ በእንጨት ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ግንብ ፡ ቢሠራበት ፡ ለእርሱ ፡ ገንዘብ ፡ ትሆናለች ። ሳይለውጣት ፡ እንደነበረው ፡ ያለ ፡ ዋጋዋን ፡ የመመለስ ፡ ዕዳ ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ.፩፻፳፱ እንስሳ ፡ ቢሆንና ፡ ቢያሰባት ፡ ወይም ፡ ተግባረ ፡ እድ ፡ ያስተማረው ፡ ባሪያ ፡ ቢሆን ፡ የተቀማው ፡ ሰው ፡ ሊመርጥ ፡ ይገባዋል ። ቢወድ ፡ ከመታደሱ ፡ በፊት ፡ በቀማኛ ፡ ዘንድ ፡

በኀበ ፡ ተዓጋሊ ። ወለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ዘተሀገ ልዎ ፡ ይደልዎ ፡ ይንሣእ ፡ ዕዳ ፡ አስብሒተ ፡ ላሕም ፡ ወትምህርተ ፡ ግብር ። ወበ ፡ ፪ቱ ፡ ፍናተ ፡ በጺሕ ፡ ኀበ ፡ ዘተደመ ፡ ወደኀኒን ፡ እምኔ ፡ ዘላ ዕሌሁ ። ወለእመ ፡ ኢተሰነአወ ፡ ለከዊነ ፡ ሚጥ ይኩን ፡ በከመ ፡ ቃለ ፡ ለዘተሀገልዎ ፡ እምኔሁ ፡ ምስለ ፡ መሐላሁ ፡ ለእመ ፡ ኢቆመ ፡ በሰምዐ ፡ ጥዩቅ ።

፩ሺ.፩፻፴ ወበቀኑዓቲስ ፡ ለዘተሀገሎ ፡ ኪያሁ ፡ እመሂ ፡ በዓስበ ፡ ዚአሁ ፡ አው ፡ በፍሬሁ ፡ አው ፡ በተ ዋልዶ ፡ እንስሳ ፡ ይንሣእ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘተሀ ገልዎ ። ወለእመ ፡ ጠፍዐ ፡ ዘተረክበ ፡ እምኔ ሆሙ ፡ በኀበ ፡ ተዓጋሊ ፡ በኀቢሮቱ ፡ አው ፡ በጕ ሕሉቱ ፡ ይደልዎ ፡ አግብአቱ ፡ መጠነ ፡ ሤጡ ። ወእመኒ ፡ ጠፍአ ፡ ዘእንበለ ፡ ፈቃደ ፡ ዚአሁ ፡ ኢይደልዎ ፡ ዕዳ ።

፩ሺ.፩፻፴፩ ወእመኒ ፡ ኮነ ፡ ዘተሀገልዎ ፡ ንዋዮ ፡ ውእቱ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ የሀቡ ፡ ምጽዋተ ፡ ለረባኒ ፡ ዚአሁ ። ወዘሂ ፡ ሰጠጠ ፡ ልብሰ ፡ ካልኡ ፡ ይፍዲ ፡ ሕጸጸ ፡ ሤጠ ፡ ዚአሁ ።
ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘበጠለ ፡ ከዊነ ፡ በቀኑዓት ፡ ቦቱ፡ ግሙራ ፡ ይደልዎ ፡ የሀብ ፡ ሤጠ ፡ አምሳሊሁ ። ወዘተሀገለ ፡ ልብሰ ፡ ዘዓዳ ፡ ወሰረየ ፡ ይኩን ፡ በከመ ፡ ኀረየ ፡ እግዚኡ ፡ ለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ይን ሣእ ፡ መጠነ ፡ ሤጡ ፡ ወእመኒ ፡ ፈቀደ ፡ ይን ሣእ ፡ ኪያሁ ፡ የሀብ ፡ ሤጠ ፡ ተሰርዮቱ ።

፩ሺ.፩፻፴፪ ወለገብርሂ ፡ ለእመ ፡ መሀሮ ፡ ግብረ ፡ ኪያ ዓታተ ፡ ኀብር ፡ የሀበ ፡ ለእግዚኡ ፡ ዘአኀረየ ፡ በግብረ ፡ እዱ ። ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ጥሪት ፡ ዘወ ሀበ ፡ እመኒ ፡ አግዐዞ ፡ አው ፡ ኀለቆ ፡ አው ፡ መጽወቶ ፡ አው ፡ አስተዋሰቦ ፡ ብእሲተ ፡ አል ቦቱ ፡ ተፈልጦ ፡ በፍትሕ ፡ ማእከሌሁ ፡ ወማ እከለ ፡ ዕጉል ፡ ዘእንበለ ፡ ዳእሙ ፡ ዘተሀገልዎ፡ አግብኦተ ፡ ሤጥ ፡ ወላዕለ ፡ ተዓጋሊ ፡ ኵሉ ፡ ፈድዮ ፡ ሤጥ ። ወለእመ ፡ ኢተክህሎ ፡ ውሂበ ፡ ኵሉ ፡ ዘተሀገሎ ፡ እመኒ ፡ ኮነ ፡ ገብረ ፡ ወአግዐዞ ወተረክበ ፡ ሎቱ ፡ መንፈቀ ፡ ሤጡ ፡ ይንሣእ ፡ ዘኮነ ፡ መላኪሁ ፡ ወይረትዕ ፡ ላዕለ ፡ ተዓጋሊ ፡ አግብአቱ ፡ መጠነ ፡ ሤጠ ፡ ረቡዑ ።

፩ሺ.፩፻፴፫ ወለእመኒ ፡ ኮነ ፡ ዘወለጠ ፡ አው ፡ መጽወቶ ፡ ሎቱ ፡ ወኢተረክበ ፡ ሤጡ ፡ አው ፡ መንፈቀ ፡ ሤጡ ፡ ወዘተሀገልዎ ፡ ይኩን ፡ በከመ ፡ ኀረየ ፡



የነበረ ፡ ዋጋውን ፡ ይውሰድ ። የቀሙት ፡ ሰው ፡ ቢወድ ፡ የላሙን ፡ የማለብትና ፡ የባረያውን ፡ የመ ማር ፡ ዋጋ ፡ ሊቀበል ፡ ይገባዋል ። ለዚህ ፡ ሁሰት ፡ መንገድ ፡ አለው ። ወደቀደመው ፡ መድ ረስና ፡ በእርሱም ፡ ላይ ፡ ካለው ፡ መዳን ፡ ነው ። በዋጋው ፡ ሁኔታ ፡ ባይስማሙ ፡ በማስረጃ ፡ ምስክር ፡ ካልጸና ፡ ከመሐላው ፡ ጋር ፡ እንደተ ቀማው ፡ ሰው ፡ ቃል ፡ ይሁን ።

፩ሺ.፩፻፴ ጥቅሙስ ፡ እርሱን ፡ ለቀሙት ፡ ሰው ፡ ይሁን ፡ በክራይ ፡ ወይም ፡ በፍሬው ፡ በእንስሳው ፡ መራ ባትም ፡ ቢሆን ፡ የቀሙት ፡ ሰው ፡ ከእርሱ ፡ ይውሰድ ። ከእነርሱ ፡ የተገኘው ፡ በቀማኛው ፡ ዘንድ ፡ በሥራው ፡ ወይም ፡ በተንኮሉ ፡ ቢጠፋ ፡ በዋጋው ፡ ልክ ፡ መመለስ ፡ ይገባዋል ። ያለ ፈቃዱ ፡ ቢጠፋበት ፡ ግን ፡ ዕዳ ፡ አይገባውም ።

፩ሺ.፩፻፴፩ የተቀማው ፡ ገንዘብ ፡ ቢሆን ፡ ለእርሱ ፡ ጥቅም ፡ ምጽዋት ፡ ሊሰጡት ፡ ይገባል ። የሌላ ውን ፡ ልብስ ፡ የቀደደ ፡ ሰው ፡ የዋጋውን ፡ ጉድ ለት ፡ ይክፈል ። በእርሱ ፡ ያለው ፡ የጥቅም ፡ ሁኔታ ፡ ፈጽሞ ፡ የጠፋ ፡ ቢሆን ፡ የመሰሉን ፡ ዋጋ ፡ ሊሰጥ ፡ ይገባዋል ። ነጭ ፡ ልብስ ፡ ቀምቶ፡ ወስዶ ፡ ቀለም ፡ ቢያገባው ፡ ጌታው ፡ እንደመ ረጠ ፡ ይሁን ። ቢወድ ፡ የዋጋውን ፡ ልክ ፡ ይው ሰድ ። እርሱንም ፡ ሊወስድ ፡ ቢወድ ፡ ቀለም ፡ የገባበትን ፡ ዋጋ ፡ ይስጥ ።

፩ሺ.፩፻፴፪ ለባሪያው ፡ ቀለም ፡ የማግባት ፡ (የመንከር) ፡ ሥራ ፡ ቢያስተምረው ፡ በእጁ ፡ ሥራ ፡ ያገኘ ውን ፡ ገንዘብ ፡ ለጌታው ፡ ይስጠው ። ስለዚህ ፡ ስለሰጠው ፡ ገንዘብም ፡ ነፃ ፡ ቢያወጣው ፡ ወይ ም ፡ ቢጐልተው ፡ ወይም ፡ ቢመጸውተው ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ ቢያጋባው ፡ በእርሱና ፡ በተቀ ማው ፡ ገንዘብ ፡ መካከል ፡ በፍርድ ፡ ልዩነት ፡ የለም ። የተቀማውን ፡ ዋጋ ፡ የሚከፍል ፡ ቢሆን ነው ፡ እንጂ ። ለቀማኛውም ፡ ሁሉ ፡ ዋጋን ፡ መክ ፈል ፡ ይገባዋል ። የቀማውን ፡ ሁሉ ፡ መስጠት ፡ ባይቻለው ፡ ባሪያም ፡ ቢሆን ፡ ነፃ ፡ ቢያወጣው ፡ የዋጋው ፡ እኩሌታው ፡ ቢገኝለት ፡ ጌታው ፡ የሆነውን ፡ ይውሰድ ። ከቀማኛ ፡ የትርፉን ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፡ መመሰስ ፡ ይገባል ።

፩ሺ.፩፻፴፫ የለወጠው ፡ ወይም ፡ የመጸወተው ፡ ቢሆን ፡ ዋጋው ፡ ወይም ፡ የዋጋው ፡ እኩሌታ ፡ ባይገኝ ፡ የቀሙት ፡ ሰው ፡ እንደመረጠ ፡ ይሁን ። ቢወድ፡

አንቀጽ ፡ ፴፯ ።

እመ ፡ ፈቀደ ፡ ያጽሐፍ ፡ ላዕሌሁ ፡ በገሪንት ፡ መጽሐፈ ፡ ዕዳ ፡ ወየሀቦ ፡ ዕድሜ ፡ እስከ ፡ ይብ ሰል ፡ በሰታፈሁ ፡ ለዝንቱ ፡ ለፈጽሞቱ ፡ ዕድሜ ፡ አው ፡ በውሂበ ፡ ምጽዋት ፡ ለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ያግብእ ። ወእመኒ ፡ ኮነ ፡ ዘእስተዋ ሰቦ ፡ አው ፡ አውሰበ ፡ ለሊሁ ፡ ኢይመውዕ ፡ ከዊነ ፡ ሚጥ ፡ ወይደልዎ ፡ ለተዓጋሊ ፡ መጠነ ፡ ሚጡ ፡ ወለእመኒ ፡ ነሥአ ፡ ኪያሃ ፡ ይፍትሖ ፡ ላዕሌሁ ፡ በመጠነ ፡ ዘአጥረየ ።

ስለ ፡ ኪራይና ፡ አከራይ ።

በዚህ ፡ የዕዳ ፡ ደብዳቤ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ይጻፍ ። ቀጠሮውን ፡ ለመፈጸም ፡ ወይም ፡ ምጽዋት ፡ ለመስጠት ፡ በእንድንት ፡ ሀብቱም ፡ እስኪሆን፡ ድረስ ፡ ቢወድም ፡ ይመልሰው ። ሚስት ፡ ያጋ ባው ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ እርሱ ፡ ቢያገባ ፡ የዋ ጋው ፡ ሁኔታ ፡ አይሻርም ። ለቀማኛው ፡ በዋ ጋው ፡ ልክ ፡ ሊከፍል ፡ ይገባዋል ። እርሷንም ፡ ቢያወጣ ፡ ባገኘው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ በእርሱ ፡ ይፍረዱ ።

---

## አንቀጽ ፴ወ፰ቱ ።

በእንተ ፡ ተዓስቦታት ፡ ወዓሳብ ፡

፩ሺ.፩፻፴፮ ጠስ ፡ ፯ቱ ፡ ፲ወ፰ቱ ፡ ፲ወ፯ቱ ፡ ወካልእኒ ። ተዓስቦስ ፡ በከዊነ ፡ ሚጣ ፡ ለበቍዔት ፡ ወተዓ ስቦትኒ ፡ ተሰናእዎ ፡ ይእቲ ፡ ላዕለ ፡ በቍዔት ፡ በተውላጥ ፡ በቃላት ። ወዘሂ ፡ ይደልዎ ፡ ይኩን ፡ መጠነ ፡ ሚጥ ፡ ጊዜ ፡ ተማይጦ ፡ ይስመ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ምጣኔ ፡ ዓስብ ፡ ዘዐስቦ ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡ በቍዔት ፡ ዘኢኮነ ፡ ሕሡመ ። ወነሥሎሙ ፡ ዘይ ደሉ ፡ ሥርዓተ ፡ ተማይጦ ፡ ማእከሌሆሙ ፡ ኢይ ቀውም ፡ ዘእንበለ ፡ በሥምረቶሙ ፡ ለተዓሳቢ ፡ ወዓሳቢ ፡ ወይኩን ፡ ዘበቍዔት ።

፩ሺ.፩፻፴፯ ወለዓሳቢስ ፡ ፪ቱ ፡ እእምሮታት ፡ ዘይትከ ሀል ፡ አወፍዮቶሙ ፡ እእምሮተ ፡ በቍዔት ፡ ለእመ ፡ ኮነት ፡ በለድሜ ፡ ወተፋጽሜት ፡ ዘከመ ተዓስቦተ ፡ ዓፀድ ፡ ለንቢሮታ ፡ ወእንስሳ ፡ ለተ ጽዕኖታ ፡ ይደሉ ፡ ለጠይቆተ ፡ ለድሜ ፡ ወፍ ጻሜት ። ወእመኒ ፡ ኮነ ፡ በገቢር ፡ ከመ ፡ ዘይት ዐስብ ፡ ብእሲ ፡ ለሰፊየ ፡ ልብስ፡ አው ፡ እን ስሳ ፡ ለዘሚረ ፡ ምንትኒ ፡ ይከውን ፡ ከመ ፡ ውሳ ኔሁ ፡ ለውእቱ ።

፩ሺ.፩፻፴፰ ወዘይደሉስ ፡ ለእወፍዮታ ፡ ከመ ፡ ዘይትዐ ስብ ፡ ምድረ ፡ ግብጻዊተ ፡ ለዘርእ ፡ ወይትዐ ወቅ ፡ ፍጻሜሃ ፡ በረውዮታ ፡ እምፈለግ ፡ ኒል ፡ ወጠረይ ፡ ማይ ፡ ላዕሌሃ ፡ ወተማኅሦተ ፡ ማይ ፡ እምኔሃ ፡ በጊዜ ፡ ዘርእ ። ወላዕለ ፡ ዘይትፌቀድ ፡ ወይደልዎ ፡ ለዘተዐሰበ ፡ ከመ ፡ ይጽሐቅ ፡ በዘይትፌቀድ ፡ ለበቍዔት ፡ ዘከመ ፡ ተመርሖ ፡ ውስተ ፡ ዓፀድ ፡ ወእስስሎተ ፡ ዘይከልእ ፡ ከዊነ፡

## አንቀጽ ፡ ፴፰ ።

ስለመከራየትና ፡ ስለአከራይ ፡ (ስለውሎታዎችና ስለአዋዋይ ፡ ይናገራል ።)

፩ሺ.፩፻፴፮ ጠስ ፡ ፯ ፡ ፲፰ ፡ ፲፯ ። ሁለተኛውም ፡ ማከራ የትስ ፡ በዋጋዋ ፡ ሁኔታ ፡ ለጥቅም ፡ ነው ። መከ ራየትም ፡ በልዋጭ ፡ ለመጠቀም ፡ በቃል ፡ መስማማት ፡ ነው ። በመገበያየት ፡ ጊዜ ፡ በዋ ጋው ፡ ልክ ፡ ሊሆን ፡ የሚገባው ፡ የተከለከለ ፡ ስላልሆነ ፡ ጥቅም ፡ ሁሉ ፡ የማከራየት ፡ ዋጋ ፡ ልክ ፡ እንዲሆን ፡ ተገባው ። በመካከላቸው ፡ የመገበያየት ፡ ሥርዓት ፡ ሊያደርጉት ፡ የሚገባ ቸው ፡ ሁሉ ፡ በተከራይና ፡ በአከራይ ፡ ፈቃድ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አይጸናም ።

፩ሺ.፩፻፴፯ ለአከራይስ ፡ ሁለት ፡ እውቀቶች ፡ (እስተያየ ቶች) ፡ እሉት ፡ ጥቅምን ፡ አውቆ ፡ እነርሱን ፡ መስጠት ፡ የሚቻል ፡ ነው ። በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ በጭራሽ ፡ ቢሆን ፡ ይኸውም ፡ በእርሻ፡ ለመኖር ፡ቦታን ፡ ለመጫን ፡ እንስሳን ፡ እንደ መከራየት ፡ ነው ። ቀኑንና ፡ መንገዱን ፡ መረ ዳት ፡ ይገባል ። በሥራም ፡ ቢሆን ፡ ልብስ ፡ ለማ ሰፋት ፡ ሰውን ፡ ወይም ፡ ማናቸውን ፡ ለመጫን እንስሳን ፡ እንደተከራዩ ፡ ቢሆን ፡ ውሳኔው ፡ እንደዚሁ ፡ ይሆናል ።

፩ሺ.፩፻፴፰ እርሷን ፡ (ቀን) ፡ ለመስጠት ፡ የሚገባስ ፡ ዘር፡ ለመዝራት ፡ የግብፅን ፡ ምድር ፡ እንደሚጠመን ያለ ፡ ቢሆን ፡ ነው ፡ ፍጻሜዋም ፡ ከዐባይ ፡ ውሀ፡ በመጠጣቷ ፡ በእርሷ ፡ ላይም ፡ ውሀ ፡ በመው ረዱ ፡ ጊዜ ፡ በዘርና ፡ በሚሻውም ፡ ነገር ፡ ጊዜ ፡ ባሕረ ፡ ሽሽ ፡ በመሆንዋ ፡ ነው ። ያከራዩት ፡ ሰው ፡ ለጥቅም ፡ በሚያሻው ፡ ነገር ፡ ሊተጋ ፡ ይገባዋል ። ይኸውም ፡ ቦታ ፡ ተመርቶ ፡ ግንዘ

በቍዔት ፡ ለአጥርዮታት ፡ ወእንስሳት ፡ ዘመ ፍቅድ ። ወዘሂ ፡ ይነሥእ ፡ ተዓሳቢ ፡ ለበቍዔተ ዚእሁ ፡ እምድኅረ ፡ ተሥዕረ ፡ ተዓስቦ ፡ ይኅ ሣእ ፡ ማኅየበ ፡ ዓዘቅት ፡ ወሐብለ ፡ ዚእሁ ። ወኢያደሉ ፡ ተዓስቦተ ፡ ሕሩማት ፡ ዘከመ ፡ መስ ቆቅዋት ፡ ወሰብእ ፡ ሥራይ ፡ ወኢዲናራት ፡ ወጠፋልሐት ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ረዳኤ ፡ ርዴ ፡ ውእቱ ።

፩ሺ፩፻፴፯ክፍል ፡ ተዓስቦሰ ፡ እምርት ፡ እመሂ ፡ ኮለንታሃ እው ፡ መንፈቀ ፡ ዚአሃ ፡ ወእወፍዮተ ፡ በቍዔ ትሰ ፡ ኢይደልዎሙ ፡ ለሰፋዪ ፡ ወለሐሣቤ ፡ እል ባስ ፡ ወለበዓለ ፡ እቶን ፡ ኅባዚ ፡ ወለእለ ፡ ይመስ ልዎሙ ፡ ከመ ፡ ይኅሥሡ ፡ ዓስቦሙ ፡ እምቅ ድመ ፡ ይፈጽሙ ፡ ግብሮሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ዳእሙ ለእመ ፡ ፈጸሙ ፡ በዝንቱ ።

፩ሺ፩፻፴፰ወለበዓለ ፡ ዓፀድ ፡ እምድኅረ ፡ ተሰነአወ ፡ በተዓስቦታ ፡ እመሂ ፡ ኀደሩ ፡ ባቲ ፡ አው ፡ ዘኢኀደሩ ፡ ባቲ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይትኀሠሥ ፡ ዓስበ ፡ ኅድረታ ፡ እምእለ ፡ ተሰነአዎሙ ፡ በበዕ ለቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ዳእሙ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ተሰናእ ዎቶሙ ፡ ወአእምሮቶሙ ፡ ገሃደ ፡ ይትኀሠሥ ፡ ለለወርኁ ።

፩ሺ፩፻፴፱ወኵሉ ፡ በዓለ ፡ ግብረ ፡ እድ ፡ ይደልዎ ፡ እኀ ዞቱ ፡ እመላኪሁ ፡ እስከ ፡ ይነሥእ ፡ ዕሤቶ ፡ ዘከመ ፡ ሴራዪ ፡ ወነሃቤ ፡ ብሩር ፡ ወለእመኒ ፡ ተኀጕለ ፡ በኀቤሁ ፡ ዘእንበለ ፡ ተኀይዮ ፡ በእን ቲአሁ ፡ ወኢ ፡በተጓሕልዎ ፡ ኢይደልዎ ፡ ዕዳ ፡ አላ ፡ ይኅድግ ፡ ዓስቦ ።

፩ሺ፩፻፵ ወዘሂ ፡ ተዐለበ ፡ ምንተኒ ፡ ወማሰነ ፡ በኀቤሁ ፡ ወለእመ ፡ ኢኮነ ፡ ዘተዐሰብዎ ፡ ይወፅእ ፡ እም ተሰናእዎ ፡ ወኢኮነ ፡ ሙስናሁ ፡ በተጓሕልዎ ፡ ወኢበተኀይዮ ፡ ኢይደልዎ ፡ ዕዳ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ተሰናእዎ ፡ ከመ ፡ ኢያንድድ ፡ እሳተ ፡ ወአ ንደደ ፡ ይደልዎ ፡ ዕዳ ። ወከማሁ ፡ ይንሣእ ፡ ዋሕሰ ፡ መስተገብር ፡ እንበለ ፡ ይውጥን ፡ ግብረ ቤት ፡ በረኪበ ፡ ሣሰር ፡ ወሰፅ ።

፩ሺ፩፻፵፩ ወለእመ ፡ እክበደ ፡ በዓለ ፡ ሐመር ፡ ፆረ ፡ ሐመሩ ፡ ዘእንበለ ፡ ምክረ ፡ አብያጺሁ ፡ አው ፡ በጊዜ ፡ ዘኢይደሉ ፡ አው ፡ ኀበ ፡ ሐመር ፡ እንተ ፡ ኢትኀኒ ፡ ይደልዎ ፡ ዕዳ ፡ ወለእመ ፡ ኢተኀየየ ፡ ኢይደልዎ ፡ ዕዳ ።

፩ሺ፩፻፵፪ ወለእመ ፡ ነሥአ ፡ ብእሲ ፡ እብነ ፡ ከመ ፡

ብና ፡ የሚሻውን ፡ እንስሳ ፡ ለማግኘት ፡ የጥቅ ምን ፡ ሁኔታ ፡ የሚከለክለውን ፡ ማስወገድ ፡ ነው ። ተከራይ ፡ ለጥቅሙ ፡ የወሰደውን ፡ የውሀ መቅጃና ፡ ገመድ ፡ መከራየቱ ፡ ከቀረ ፡ በኋላ ፡ ይውሰድ ። የተከለከሉትንም ፡ መከራየት ፡ አይ ገባም ። ይኸውም ፡ እንደእስለቃሾች ፡ (እንደ ሙሾ ፡ አውጭዎች) ፡ ሥራይ ፡ እንደሚያደ ርጉ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ዲናር ፡ እንደ ፡ ተመዘነ ፡ ያለ ፡ ነው ። ይህ ፡ ያረጣ ፡ ረዳት ፡ ነውና ።

፩ሺ፩፻፴፯ ክፍል ፡ መከራየትስ ፡ መላዋን ፡ ወይም ፡ እኩ ሌታዋን ፡ ቢሆን ፡ የታወቀች ፡ ናት ። ጥቅም ፡ መስጠት ፡ ግን ፡ ለሰፊ ፡ ለልብስ ፡ አጣቢ ፡ ለእ ንጀራ ፡ ጋጋሪ ፡ እነርሱንም ፡ ለመሰሉ ፡ ሥራ ቸውን ፡ ከመፈጸማቸው ፡ በፊት ፡ ዋጋቸውን ፡ ሊጠይቁ ፡ አይገባቸውም ። ይህን ፡ ቢፈጽሙ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፩ሺ፩፻፴፰ ለባለቦታ ፡ በመከራየቱዋ ፡ ከተዋዋለ ፡ በኋላ ፡ ቢያድሩባትም ፡ ወይም ፡ ባያድሩባት ፡ ከተዋዋላቸው ፡ ሰዎች ፡ ያደሩባትን ፡ ኪራይ ፡ በየቀኑ ፡ ሊፈላለግ ፡ ይገባል ። በየወሩ ፡ እንዲቀ በል ፡ አውቀው ፡ በግልጽ ፡ የተስማሙ ፡ ቢሆን፡ ነው ፡ እንጂ ።

፩ሺ፩፻፴፱ ባለተግባረ ፡ እድ ፡ ሁሉ ፡ ከገኘው ፡ ዋጋ ውን ፡ እስኪቀበል ፡ ድረስ ፡ ሊይዝ ፡ ይገባዋል ። ይኸውም ፡ እንደ ፡ ቀለም ፡ አጣቢ ፡ እንደ ፡ ብር፡ እንጥረኛ ፡ ያለ ፡ ነው ። ስለ ፡ እርሱ ፡ ያለ ፡ ቸል ታና ፡ ያለተንኮል ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ቢጠፋም ፡ ዋጋውን ፡ ይተዉ ፡ እንጂ ፡ ዕዳ ፡ አይገባውም ።

፩ሺ፩፻፵ ማናቸውንም ፡ የተከራየ ፡ ሰው ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ቢጠፋ ፡ የተከራዩት ፡ ከስምምነት ፡ የወጣ ፡ ካልሆነ ፡ ጥፋቱም ፡ በተንኮልና ፡ በቸ ልታ ፡ ካልሆነ ፡ ዕዳ ፡ አይገባውም ። እሳት ፡ እንዳያነድ ፡ ስምምነት ፡ ቢሆን ፡ ቢያነድም ፡ ዕዳ ፡ ይገባዋል ። እንደዚሁም ፡ ሠራተኛ ፡ ሣርና ፡ እንጨት ፡ በማግኘት ፡ ቤት ፡ ሥራን ፡ ሳይጀምር ፡ ዋስ ፡ ይቀበል ።

፩ሺ፩፻፵፩ ባለመርከብ ፡ ያለጓደኞቹ ፡ ምክር ፡ ወይም ፡ በማይገባ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ በማትገባ ፡ መርከብ ፡ የመርከቡን ፡ ጭነት ፡ ቢያከብድ ፡ ዕዳ ፡ ይገባ ዋል ። ቸል ፡ ባይል ፡ ግን ፡ ዕዳ ፡ አይገባውም ።

፩ሺ፩፻፵፪ ሰው ፡ ሊሸከመው ፡ ወይም ፡ ሊጠርብ ፡ ድን

ይፁር ፡ እሙ ፡ ከመ ፡ ይጸርብ ፡ ወለእመ ፡ ተሰብረ ፡ በሕጸጸ ፡ እእምሮቱ ፡ ይደልዎ ፡ ዕዳ ፡ እሙ ፡ አልቦ ።

፩ሺ.፩፻፵፫ ወለእመ ፡ አማሰነ ፡ አንጹዋ ፡ ምንተኒ ፡ እምነ ዘይሚጥውዎ ፡ ለሐፃቢ ፡ አልባስ ፡ ይደልዎ ፡ ዕዳ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ኢርእዮ ፡ በሠናይ ፡ ዕቀባ ። ወከማሁ ፡ ዘወሀበ ፡ ፩ዱ ፡ ለካልኡ ፡ ምንተኒ ፡ ወኢዐቀበ ፡ ወገብረ ፡ ተኀጽዮ ፡ ውእቱ ። ወለእመ ኮነ ፡ ዘይትከሀሎ ፡ ከመ ፡ ይትበአስ ፡ በእንተ ፡ ዘሀለወ ፡ ኀቤሁ ፡ ወኢተበአሰ ፡ ይደልዎ ፡ ዕዳሁ ።

፩ሺ.፩፻፵፬ ወዘተዐሰበ ፡ ምንተኒ ፡ እንዘ ፡ የአምር ፡ ከመ ይረክቦ ፡ ሕሡም ፡ ለዘተዐሰበ ፡ ኪያሁ ፡ ወኢነገሮ ፡ ይደልዎ ፡ ዕዳሁ ፡ ለእመ ፡ ኢያእመረ ፡ ዐሳቢ ፡ ዘንተ ፡ ከመ ፡ ዘይኀሥሥ ፡ ወይትዐሰብ ፡ ንዋየ ፡ ሥጡቀ ፡ እሙ ፡ ምርጓየ ፡ ሥዑረ ፡ እሙ ፡ ማዩ ፡ ዘየደዊ ፡ በዘይትረዓዩ ፡ ውስቴቱ ። ወዘይኀሥሥ ፡ ዓስበ ፡ ለዐቂበ ፡ ምንትኒ ፡ ይደልዎ ፡ ዕዳ ፡ ለእመ ፡ ተኀጥአ ፡ ለዐቂቦቱ ።

፩ሺ.፩፻፵፭ ክፍል ፡ ወይደሉ ፡ ተዓስቦተ ፡ ማኅደር ፡ ወለእመ ፡ ኢተዐውቀ ፡ ዘይትገበር ፡ በውስቴታ ፡ በኀበ ፡ ኢይትገበር ፡ ዘእንበለ ፡ ዘይትዐወቅ ፡ እሙ ፡ በዘኢይብእሳ ፡ ዘእንበለ ፡ ለእመ ፡ ተሰነአወ ፡ በግቢረ ፡ ዝንቱ ፡ በከመ ፡ ይገብሩ ፡ ቤተ ፡ ሰማን ፡ ወቤተ ፡ መበስል ።

፩ሺ.፩፻፵፮ ወይደሉ ፡ ተዓስቦተ ፡ ምድር ፡ ለዘርእ ፡ ውስቴታ ፡ ይኩን ፡ በከመ ፡ ልማዶሙ ፡ ለእለ ፡ ከማሃ ። ወለእመ ፡ ኢያበየነ ፡ ዘይዘርእ ፡ ሶበ ፡ ይትፌጸም ፡ ዕድሜ ፡ ተዓስቦ ፡ ይደልዎ ፡ ለበ ሳቢ ፡ ኀሠሣሁ ፡ ለተዓሳቢ ፡ በከሊአ ፡ ሕንጸ ፡ ውተኪል ፡ እሙ ፡ ከመ ፡ ይሰነእዉ ፡ ላዕለ ፡ ሀልዎተ ፡ ሕንጸ ፡ እሙ ፡ ዘተከለ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ለመሳኪሁ ፡ ወምድርኒ ፡ ለመላኪሃ ፡ በእንተ ፡ ተማይጦ ፡ ተዓሳቢ ፡ ምድረ ፡ ወተሐድሶተ ፡ ዓስበ ፡ ምድር ፡ እሙ ፡ ሢጠ ፡ ዚአሁ ፡ ለዓስበ ፡ ምድር ፡ እሙ ፡ ተዐሰቦተ ፡ ካልእ ፡ ዘሕንጸ ፡ እሙ ፡ ዘአትክልት ።

፩ሺ.፩፻፵፯ ወብዉሕ ፡ ከመ ፡ ይሚጥ ፡ ዐሳቢ ፡ ለተዓሳቢ ፡ ዘተዐሰበ ፡ ቦቱ ፡ ወትትርፍ ፡ ዓስብ ፡ ዘተዐደ ሙት ፡ ላዕሌሁ ፡ ዘይትቀደሞ ፡ ለተማይጦ ፡ ወበ



ጋይ ፡ ቢወስድ ፡ በሰውተቱም ፡ ጉድለት ፡ ቢሰበር ፡ ዕዳ ፡ ይገባዋል ። ወይም ፡ አይገባውም

፩ሺ.፩፻፵፫ ለአጣቢ ፡ ከሰጡት ፡ ልብስ ፡ አይጥ ፡ ማናቸውንም ፡ ቢያጠፋ ፡ ለአጣቢ ፡ ዕዳ ፡ ይገባዋል ። በሰንፍና ፡ አልጠበቀውምና ። እንደዚሁም ፡ አንዱ ፡ ለሌላው ፡ ምንም ፡ ምን ፡ ሰጥቶት ፡ ባይጠብቀው ፡ ይህም ፡ ቸልታ ፡ ነው ። በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ስላለው ፡ ነገር ፡ መከላከል ፡ ሲቻለው ፡ ባይከላከል ፡ ዕዳው ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ.፩፻፵፬ እርሱን ፡ ለተከራየ ፡ ሰው ፡ ጉዳት ፡ እንደሚያገኘው ፡ እያወቀ ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ ያከራየ ፡ ሰው ፡ ባይነግረውም ፡ ተከራዩም ፡ ይህን ፡ ባያውቅ ፡ ዕዳ ፡ ይገባዋል ። ይኸውም ፡ የተሠነጠቀ ፡ ሰቃ ፡ ወይም ፡ የተፈታ ፡ ምድረ ፡ በዳን ፡ ወይም ፡ ውኃው ፡ በውስጡ ፡ የሚሰማሩትን ፡ የሚያሳምመውን ፡ እንደማከራየት ፡ ነው ። ማናቸውንም ፡ ለመጠበቅ ፡ ኪራይ ፡ የተቀበለ ፡ ሰው ፡ መጠበቁን ፡ ቸል ፡ ቢል ፡ ዕዳ ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ.፩፻፵፭ ክፍል ፡ ቤት ፡ መከራየት ፡ ይገባል ። ከሚታወቀው ፡ ወይም ፡ በማይጐዳት ፡ ገንዘብ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በማይሠራበት ፡ በውስጧ ፡ የሚሠራው ፡ ካልታወቀ ፡ የዕጣን ፡ ቤትና ፡ የማብሰያ ፡ ቤት ፡ እንደሚሠሩ ፡ በዚህ ፡ ቢስማሙ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፩ሺ.፩፻፵፮ በውስጧ ፡ ዘር ፡ ለመዝራት ፡ ምድር ፡ መጠመን ፡ እንደ ፡ እርሷ ፡ ባሉ ፡ ምድሮች ፡ ልማድ ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ። የሚዘራ ፡ ባይናገር ፡ የመጠመን ፡ ወራት ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ አስጠማኝ ፡ ተጠማኙን ፡ ሕንፃውንና ፡ ተክሉን ፡ በመከልከል ፡ ወይም ፡ በሕንፃው ፡ ወይም ፡ በተክሉ ፡ መኖር ፡ እንዲስማሙ ፡ ሊፈላስገው ፡ ይገባዋል ። ተክሉ ፡ ለባለቤቱ ፡ ምድርም ፡ ለባለ ፡ ርስቱ ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ። ተጠማኝ ፡ ምድርን ፡ ስለመግባትና ፡ ስለምድሩ ፡ ዋጋ ፡ ወይም ፡ ስለምድሩ ፡ ኪራይ ፡ ዋጋ ፡ መታደስ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ሌላ ፡ የሕንጻ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አትክልት ፡ ቦታ ፡ መከራየት ፡ ይናገራል ።

፩ሺ.፩፻፵፯ አከራይ ፡ ለተከራይ ፡ የተከራየበትን ፡ ሊሸጥ ፡ ይገባዋል ። መግቢያዋትን ፡ የሚቀድመው ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ የተቀጠረችበት ፡ ኪራይ ፡ ትቅር ።

ሕቱ ፡ ይስእሎ ፡ ጊዜ ፡ ተማይጦ ፡ ይመይጦ ፡ ተዓስቦ ። ወለእመ ፡ ተወለጠ ፡ ተዓሳቢ ፡ ሳእለ ፡ ዘይሜይጥ ፡ ይኩን ፡ በከመ ፡ ኀረየ ፡ ተዓሳቢ ፡ በውስተ ፡ ዓስብ ። ወእመኒ ፡ ኢያእመረ ፡ ተማ ያጢ ፡ በተዓስቦ ፡ ይኩን ፡ በከመ ፡ ኀረየ ፡ ለከ ዊን ፡ ሚጥ ፡ እው ፡ ለእብጥሎታ ።

ነገር ፡ ግን ፡ በመገበያየት ፡ መከራየት ፡ በቀረ ፡ ጊዜ ፡ ይስማሙ ። ተከራይ ፡ በሚገዛው ፡ ላይ ፡ ቢለውጥ ፡ በኪራይ ፡ ተከራይ ፡ እንደመረጠ ፡ ይሁን ።

፩ሺ፩፻፵፰ ወይደሉ ፡ ተዓስቦቶ ፡ እንስሳ ፡ ለተሰብሳ ፡ እው ፡ ለፀዊር ፡ በከመ ፡ ልማድ ፡ ወዘከማሁ ፡ ከማሁ ። ወለእመ ፡ ኢያጠየቀ ፡ ዘይጼሀን ፡ እው ፡ ዘያዐውር ፡ ዘተሰነአወ ፡ ቦቱ ፡ በግብር ፡ እሙር ፡ ኢይክውኖ ፡ ለዘተሀሰበ ፡ ከመ ፡ ይወልጥ ፡ ኪያሁ ፡ ወእርእያሁ ፡ ዘእንበለ ፡ በአቅ ልሎ ፡ ክበድ ፡ እምነቢሁ ፡ ከመ ፡ ዘይትዐሰብ ፡ እንስሳ ፡ ከመ ፡ ያጹሩ ፡ መክሊተ ፡ ጥጥ ፡ ኢይ ደልዎ ፡ ከመ ፡ ያሁሩ ፡ መክሊተ ፡ ሐፂን ፡ ወኢ ፡ ዘያሬይፍድ ፡ እመጠን ፡ ዘተወሰነ ፡ ሎቱ ፡ በዐ ቅም ።

፩ሺ፩፻፵፰ ለመጫን ፡ ወይም ፡ እንደልማዱ ፡ ለማሸ ከም ፡ እንስሳ ፡ መከራየት ፡ ይገባል ። ይኸውም ፡ እንደ ፡ እርሷ ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ እርሱ ፡ ነው ። የሚጫን ፡ ወይም ፡ የሚያሸክም ፡ ሰው ፡ በታወ ቀ ፡ ሥራ ፡ የተስማማበትን ፡ ባያረጋግጥ ፡ ሸክ ሙን ፡ ከእርሱ ፡ በማቅለል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የተ ከራየውን ፡ ዓይነቱንና ፡ መልኩን ፡ ሊለውጥ ፡ አይገባውም ። የጥጥ ፡ መክሊት ፡ ሊያሸክማት ፡ እንስሳ ፡ ተከራይቶ ፡ የብረት ፡ መክሊት ፡ ወይ ም ፡ ከተወሰነው ፡ ልክ ፡ የሚበዛ ፡ ሊያሸክማት ፡ እንደማይገባ ፡ ነው ። በልክ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፩ሺ፩፻፵፱ ወዘሂ ፡ ተሀሰበ ፡ እንስሳ ፡ በሐዊረ ፡ ፍኖት ፡ እሙር ፡ ወዐደወ ፡ ኪያሃ ፡ ለእመ ፡ ገብረ ፡ ዘንተ ፡ ይረክቦ ፡ ስዳ ፡ አማስኖታ ፡ ዘእንበለ ፡ ዳእሙ ፡ ለእመ ፡ አእመረ ፡ መሳኪሃ ፡ ዘንተ ፡ ወኢከልኦ። ወለእመ ፡ ተኀጥአ ፡ እምዖረ ፡ እንስሳ ፡ ምን ትኒ ፡ እምዘ ፡ ተሰነአወ ፡ ላዕሌሁ ፡ ከመ ፡ ስንቅ ወዘይመስሎ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይንሣእ ፡ ዘተዐ ሰበ ፡ ህየንቴሁ ፡ በእምሳለ ፡ ዚአሁ ፡ ዘእንበለ ፡ ለእመ ፡ ተሰነአወ ፡ በካልእ ፡ እምዝንቱ ።

፩ሺ፩፻፵፱ የታወቀ ፡ መንገድ ፡ ለመሄድ ፡ እንስሳን ፡ የተከራየ ፡ ሰው ፡ ከዚያም ፡ ቢያልፍ ፡ ያህን ፡ ቢያደርግ ፡ ባለቤቱ ፡ ይህን ፡ እውቆ ፡ ባይከለክ ለው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እርሷን ፡ የማጥፋት ፡ ስዳ ፡ ያገኘዋል ። ከእንስሳው ፡ ጭነት ፡ ከተስማሙ በት ፡ እንደስንቅና ፡ እንደመሰለው ፡ ያለ ፡ አን ዳች ፡ ነገር ፡ ቢጠፋ ፡ የተከራየው ፡ ስለእርሱ ፡ ፈንታ ፡ በመሰሉ ፡ ሊቀበል ፡ ይገባዋል ። ከዚህ ፡ በሌላ ፡ የተስማሙ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ።

፩ሺ፩፻፶ ክፍል ፡ በእንተ ፡ ዘይሠዐር ፡ ተዓስቦ ። ወእም ከመ ፡ ተፈጸመት ፡ ሰድሜ ፡ ተዓስቦ ፡ በጠለ ፡ ወይቀውም ፡ ሤጠ ፡ ምሳሌ ፡ ወከማሁ ፡ ለእመ ፡ ኮነት ፡ ሤጠ ፡ ተዓስቦ ፡ ሙስንተ ፡ ወዘተዐሰበሰ ዓፀደ ፡ ወረከበ ፡ ነውረ ፡ በውስቴታ ፡ ዘይከ ውን ፡ ሕሠመ ፡ ለንዋር ፡ ይከውኖ ፡ ከመ ፡ ይሥ ዐር ። ወእምከመ ፡ ተዳደቀ ፡ ነውር ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይሥዐር ፡ በጊዜ ፡ ተዳድቆቱ ፡ ለዘእደብ ቍስ ፡ ወከማሁ ፡ ተረፈ ፡ በቋስዮት ፡ ወለእመ ፡ ሞተ ፡ ዐሳቢ ፡ እው ፡ ተዓሳቢ ፡ ወከነ ፡ ተሰና እዎቱ ፡ ምስለ ፡ ካልኡ ፡ ተሠዐረት ፡ እንከ ።

፩ሺ፩፻፶ ክፍል ፡ መከራየት ፡ ስለሚቀርበት ፡ ይናገራል። የመከራየት ፡ ቀጠሮ ፡ ከተፈጸመች ፡ ዘንድ ፡ ፈረሰ ፡ የመሰለውም ፡ ዋጋ ፡ ይተካል ። የመከ ራየት ፡ ዋጋ ፡ መጥፎ ፡ ብትሆን ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ፡ ቤቷ ፡ የተከራየ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ለማደር ፡ ጥፋት ፡ የሚሆን ፡ ነውር ፡ በውስጧ ፡ ቢያገኝ ባት ፡ ሊያፈርስ ፡ ይገባዋል ። ድንገት ፡ ነውር ፡ ቢያገኘው ፡ ነውር ፡ ድንገት ፡ ባገኘው ፡ ጊዜ ፡ የማይጠቅመውን ፡ ሊያፈርስ ፡ ይገባዋል ። የቀ ቅሙም ፡ ትርፍ ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። አከራይ ፡ ወይም ፡ ተከራይ ፡ ቢሞት ፡ ስምምነቱ ፡ ከሌ ላው ፡ ጋር ፡ ቢሆን ፡ እንግዲህ ፡ ተሻረች ።

፩ሺ፩፻፶፩ ክፍል ፡ ወይደሉ ፡ ሰዓት ፡ ለሐናጺ ፡ እም ድኅረ ፡ ፈጸመ ፡ ሕንጻሁ ፡ ወእመ ፡ እኮ ፡ ይን ሣእ ፡ ዋሕሰ ። ወይደሉ ፡ ከመ ፡ ይሜጥ ፡ ሰዓተ፡ ዘአጥረየ ፡ በተገብሮቱ ፡ በኵሉ ፡ መዋዕለ ፡ ሕይ ወቱ ። ወዝንቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ይደሉ ፡ ለሠያጢ ፡

፩ሺ፩፻፶፩ ክፍል ፡ ሥራውን ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ለአናጺ፡ ዋጋው ፡ ይገባዋል ። ያህም ፡ ባይሆን ፡ ዋስ ፡ ይቀበል ፡ ባለ ፡ ዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ በሥራው ፡ ያገኘ ውን ፡ ገንዘብ ፡ ሊሸጥ ፡ ይገባዋል ። ይህ ፡ ትእ ዛዝ ፡ ለሻጭም ፡ ለገዥም ፡ ይገባል ። ያልሠራ

ወለተማየጠ ፡ ወለእመ ፡ ሜጠ ፡ ዘእንበለ ፡ ስማዕቱ ፡ ዘኢገብረ ፡ ወእእመረ ፡ ተማየጠ ፡ ይደልዎ ፡ እበሳ ፡ ሎቱ ፡ ወእመሰ ፡ ኢያእመረ ፡ እልቦቱ ፡ ዕዳ ፡ ሳዕሌሁ ፡ ለዘተማየጠ ፡ ዘከመ ፡ እንስሳ ፡ ወበቅል ፡ ወበግዕ ፡ ወዘይመስልዎሙ፡ ለእሉ ፡ እንስሳት ፡ እው ፡ ንዋያት ፡ ወባሕቱ ፡ ይኩን ፡ ዘይሠይጥ ፡ ወዘይማየጥ ፡ በእእምሮተ ፡ ሰማዕት ፡ ማእምራን ።

፩ሺ፩፻፶፪ ክፍል ፡ ወለእመ ፡ ጠፍአ ፡ ስሜቱ ፡ ለመስተ ገብር ፡ እምድኅረ ፡ ጸመወ ፡ ብዙኀ፡ መዋዕለ ፡ ወለእመ ፡ ተረክበ ፡ ቦቱ ፡ ነውር ፡ ዘኢይደሉ ፡ ይደሉ ፡ ሎቱ ፡ ስሜተ ፡ ጻምዎቱ ፡ ዘከመ ፡ ተወ ሰነ ፡ በዓቅም ፡ በእምጣነ ፡ ደለውዎ ፡ ወስሜ ትሰ ፡ ለእመ ፡ ተእመነት ፡ ወቆመት ፡ ቈመተ ፡ እምሳል ። ወከማሁ ፡ ለእመ ፡ ኮነት ፡ ስሜት ፡ ጥፍእተ ፡ እምነ ፡ ዘከልእ ፡ ዓሰበ ፡ ዓፀድ ፡ ወተ ረክበ ፡ ባቱ ፡ ነውር ፡ ዘኢይነኪ ፡ በማኅደር ፡ ውእቱ ፡ ጥፉእ ፡ ለእመኒ ፡ ተረክበ ፡ ቦቱ ፡ ነውር ፡ ውእቱ ፡ ጥፉእ ፡ ኢይማኒ ፡ ወከማሁ ፡ ተረፈ ፡ በቋሚያት ። ወለእመ ፡ ሞተ ፡ በሳቢ ፡ እው ፡ ተዓሳቢ ፡ ወኮነ ፡ ተሰናእዎታ ፡ ምስለ ፡ ካልኡ ፡ ተሥዕረት ፡ እንከ ።

፩ሺ፩፻፶፫ ወዘሂ ፡ ተዓሰበ ፡ ዓፀደ ፡ ለለዙሉ ፡ እውራኅ፡ በዲናር ፡ ወኢያእመረ ፡ ኍልቈ ፡ ዙሎን ፡ እው ራኅ ፡ ይከውኖ ፡ ለተዓሳቢ ፡ እምድኅረ ፡ ፩ዱ ፡ ወርኅ ፡ ከመ ፡ ያብጥል ፡ ሥርዓተ ፡ ተዓስቦ ። ወይደሉ ፡ ሥርዓተ ፡ ኅሬ ፡ በተዓስቦ ፡ መዋ ዕለ ፡ እሙረ ፡ ወእብጥሎታሂ ፡ ወለእመኒ ፡ ተኀ ደደ ፡ ንዋይ ፡ ዘተዐስብዎ ፡ እው ፡ ተዳደቀ ፡ ዘይከልእ ፡ ከዊነ ፡ በቀዋሚት ፡ ቦቱ ፡ ይሠዐር ፡ ዓስብ ፡ እምነ ፡ ተዓሳቢ ፡ በተረፈ ፡ ዕደሚሁ ፡ ዘየንተ ፡ ዘኀለፈ ፡ እምኔሃ ፡ ዘእንበለ ፡ ዳእሙ ፡ ለእመ ፡ እግብኡ ፡ እምኔሁ ፡ በከመ ፡ ውእቱ ፡ ጊዜ ። ወምክንያት ፡ ከመ ፡ ያበዋሉ ፡ ለተዓሳ ቢ ፡ በዘተርፈ ፡ እምነ ፡ ዘኀለፈ ፡ ወነሥሎሙ ፡ ይትባእሉ ፡ ኀበ ፡ ተከልአ ፡ እምበቍዔት ፡ ዘእን በለ ፡ ኀርየት ።

፩ሺ፩፻፶፬ ወዘእንተ ፡ ተዓሰቦስ ፡ ለእመ ፡ ተበሰበ ፡ ዓፀደ ፡ በዕድሚሁ ፡ ወእምዝ ፡ እኀዝዎ ፡ በዕዳ ፡ እምቅድመ ፡ ፍጻሜሃ ፡ ወለእመ ፡ እልቦቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ሜጠ ፡ ዘእሃ ፡ ይፍዲ ፡ ኪያሁ ፡ እው ፡ ለእመ ፡ እግዐዞ ፡ ለዘተዐሰበ ፡ እው ፡ ጕለቶ ፡ እው ፡ መጽዐተ ፡ ቦቱ ፡ ወዘሂ ፡ ጕኮእ ፡ በኢ



ውን ፡ ያለዋጋው ፡ ቢሸጥ ፡ ገዥም ፡ ቢያውቅ ፡ ዕዳ ፡ የለበትም ። ይኸውም ፡ እንደ ፡ እንስሳ ፡ እንደ ፡ በቅሎ ፡ እንደ ፡ በግ ፡ እነዚህንም ፡ እንስሳ ት ፡ እንደሚመስሏቸው ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ገን ዘብ ፡ ያለ ፡ ቢሆን ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ የሚሸ ጥም ፡ የሚገዛም ፡ በሚያውቁ ፡ ምስክሮች ፡ አስረጅነት ፡ ይሁን ።

፩ሺ፩፻፶፪ ክፍል ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ከደከመ ፡ በኋላ ፡ የሠራ ተኛ ፡ ደመወዝ ፡ ቢጠፋ ፡ የማይገባም ፡ ነውር ፡ ቢገኝበት ፡ በገመቱት ፡ ልክ ፡ እንደተወሰነው ፡ መጠን ፡ የድካሙ ፡ ዋጋ ፡ ይገባዋል ። ዋጋስ ፡ ብትታመንና ፡ እምሳያውን ፡ በመተካት ፡ ብት ጸና ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ ዋጋ ፡ ከሌላው ፡ ቤት፡ ዋጋ ፡ የጠፋች ፡ ብትሆን ፡ በቤቱም ፡ የማይጐ ዳ ፡ ነውር ፡ ቢገኝበት ፡ ጥፋ ፡ ነው ። ነውር ፡ ቢገኝበትም ፡ ያ ፡ ጥፋው ፡ አያምርም ። የጥቅ ሙም ፡ ትርፍ ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። አከራይ ፡ ወይም ፡ ተከራይ ፡ ቢሞት ፡ በእርሷ ፡ መስማ ማቱ ፡ ከሌላው ፡ ጋር ፡ ቢሆን ፡ እንግዲህ ፡ ፈረ ሰች ።

፩ሺ፩፻፶፫ በየወሩ ፡ ሁሉ ፡ በዲናር ፡ ቦታ ፡ የተከራየ ፡ የወሮቹን ፡ ሁሉ ፡ ቁጥር ፡ ባያውቅ ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ ለተከራዩ ፡ የክራዩን ፡ ውል ፡ ሊያ ፈርስ ፡ ይገባዋል ። በታወቀ ፡ ቀን ፡ በመከራየት በማፍረስ ፡ የምርጫ ፡ ደንብ ፡ ይገባል ። የተከ ራዩት ፡ ገንዘብም ፡ ቢዘረፍ ፡ ወይም ፡ በእርሱ ፡ ያለውን ፡ የጥቅሙን ፡ ሁኔታ ፡ የሚከለክል ፡ ድንገተኛ ፡ አደጋ ፡ ቢገጥመው ፡ ከእርሷ ፡ ስላ ለፈው ፡ በቀጠሮው ፡ መቅረት ፡ (ማለፍ) ፡ ኪራይ ፡ ከተከራይ ፡ ይቀራል ። እንደዚያው ፡ ጊዜ ፡ ከእርሱ ፡ (ውሉን) ፡ ቢመልሱ ፡ ነው ፡ እን ጂ ። የታወቀ ፡ ምክንያት ፡ ካለፈው ፡ በቀረው ፡ ተከራይን ፡ ያስቀረዋል ። ሁሉም ፡ ያለምርጫ ፡ ከጥቅም ፡ ወደ ፡ መከልከል ፡ ይመለሳሉ ።

፩ሺ፩፻፶፬ ስለመከራየትስ ፡ በቀጠሮ ፡ (በውሳኔ) ቦታ ፡ ቢከራይ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ከመፈጸሟ ፡ በፊት ፡ በዕዳ ፡ ቢያዝ ፡ ከዋጋውም ፡ በቀር ፡ ባይኖረው ፡ እርሱኑ ፡ ይክፈል ። ወይም ፡ ነፃ ፡ ቢያወጣው ፡ ወይም ፡ ቢጕልተው ፡ ወይም ፡ ቢመጸውተው ፡ ስለእርሱም ፡ ቢቸኩል ፡ ይመልሰው ። በራሱ ፡

አንቀጽ ፡ ፴፯ ።

ንቲአሁ ፡ ያግብእ ። ወዘሂ ፡ ጕየ ፡ እምተዓስ ቦተ ፡ ርእሱ ፡ እው ፡ እምተዓስቦተ ፡ ንዋይ ፡ ክቡድ ፡ ዘጕየ ፡ ወእምከመ ፡ ረከበ ፡ ተዓሳቢ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይትኃሠሥ ፡ ወይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይሢጥ ፡ እምእንስሳሁ ፡ ወይክፍል ፡ ላዕሌሃ ፡ በትእዛዘ ፡ መኰንን ፡ ወያስተዋፅእ ፡ ኪያሃ ፡ በእንተ ፡ ሊቃሕ ፡ ዘላዕሌሁ ፡ በቅድመ ፡ ሰማ ዕት ።

፩ሺ፩፻፶፭ ወበእንተሰ ፡ ተዓሳቢ ፡ እመቦ ፡ ዘተዐሰበ ፡ ዓፀደ ፡ ከመ ፡ ይኅድር ፡ ውስቴታ ፡ ወእኅዘ ፡ ይንግድ ፡ እው ፡ ተዐሰበ ፡ እንስሳ ፡ ከመ ፡ ይን ግድ ፡ ባቲ ፡ ወእፅርዐ ፡ ንግደቶ ፡ እው ፡ ተዐ ሰበ ፡ ቤተ ፡ ዘይሠይጥ ፡ ቦቲ ፡ ወይሣየጥ ፡ ወጠ ፍአ ፡ ንዋዩ ። ወሕፃንኒ ፡ ለእመ ፡ ሞተ ፡ እም ድኅረ ፡ ተሰናእዎ ፡ በተዓስቦ ፡ ለእጥብዎቱ ፡ እው ፡ እበየ ፡ ጠቢወ ፡ እው ፡ ብእሲት ፡ ለእመ ፡ እበየት ፡ እጥብዎቶ ።

፩ሺ፩፻፶፮ ክፍል ፡ ወቦቱ ፡ ኍልቈ ፡ ጸዋትው ፡ ወይደ ልዎ ፡ ለተዓሳቢ ፡ ከመ ፡ የሀብ ፡ ለዓሳቢ ፡ በእ ምጣነ ፡ ዓስቡ ፡ ዘተዐሰበ ፡ ቦቲ ፡ ወእብዝኖስ ፡ ወእሕጽጾ ፡ እምከመ ፡ ተሰነአወ ፡ ከመ ፡ ኢያእ በይ ፡ ይኩን ፡ ከማሁ ። ወለእመ ፡ እንበረ ፡ ፩ዱ ፡ ብእሲ ፡ ተሐባዬ ፡ ምንተኒ ፡ በእንተ ፡ ንዋይ ፡ በበይነ ፡ ረኃብ ፡ ወእምዝ ፡ ተሴሰየ ፡ ወእምዝ ፡ እምድኅረ ፡ ዓመት ፡ ኮነ ፡ ጽጋብ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ያገብእ ፡ ወይነሥእ ፡ ዘእንበረ ፡ ወእ መኒ ፡ መጽአ ፡ ረኃብ ፡ በደኃሪ ፡ ዓመት ፡ ያኅ ድግ ፡ በውስቴታ ፡ ካለበ ።

፩ሺ፩፻፶፯ ወዘተሐበየ ፡ በምንትኒ ፡ እምንዋይ ፡ አል ቦቱ ፡ ዕዳ ፡ በዘይከውን ፡ ላዕለ ፡ ፍሬያት ፡ እመ ዓተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘያማስን ፡ እላ ፡ ዘይደል ዎስ ፡ ለዳ ፡ በዘኮነ ፡ ማእከላየ ፡ እምነ ፡ ዝንቱ ፡ ወተሐባዪስ ፡ በዘይከፍሎ ፡ ለካልእ ፡ ወይእ ኀዞ ፡ ለዳ ፡ በንዋየ ፡ ተሳትፎ ፡ ከመ ፡ ይክፍሎ ፡ በረባኅኒ ፡ ወበኅጕልኒ ። ወለእመ ፡ ኀደገ ፡ ተሐባዪ ፡ ለዓፀድ ፡ እንተ ፡ ተሐበየ ፡ ኪያሃ ፡ ዘእንበለ ፡ ምክንያት ፡ እምቅድመ ፡ ፍጻሜ ፡ ሰድሜ ፡ ይነብር ፡ ውእቱ ፡ በተሐብዮ ፡ እስከ ፡ ተፍጻሜተ ፡ ሰድሜሁ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ተሰና እዎ ፡ ከመ ፡ ይሠየም ፡ በዓለ ፡ ግብረ ፡ እድ ፡ ንሕነ ፡ ነኀሥሥ ፡ ተሠይሞተ ፡ ብእሲ ፡ ኄር ፡ ለዝንቱ ።

ስለ ፡ ኪራይና ፡ አከራይ ።

ከመከራየት ፡ የሸሸ ፡ ወይም ፡ ከከባድ ፡ ገንዘብ ፡ መከራየት ፡ የተነሳ ፡ የሸሸ ፡ ተከራዩን ፡ አከራይ ቢያገኘው ፡ ሊፈላለገው ፡ ይገባዋል ። ከእንስሳ ዎቹም ፡ ሸጠ ፡ በዳኛ ፡ ትእዛዝ ፡ ሊከፍል ፡ ይገ ባዋል ። በምስክር ፡ ፊት ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ስላ ለው ፡ ብድር ፡ እርሷን ፡ ያወጣጣት ።

፩ሺ፩፻፶፭ ስለተከራይስ ፡ እንዲህ ፡ ነው ። በውስጧ ፡ ሊያድር ፡ ቦታ ፡ የተከራየ ፡ ቢኖር ፡ ሊነግድባ ትም ፡ ቢጀምር ፡ ወይም ፡ ይነግድባት ፡ ዘንድ ፡ እንስሳ ፡ ቢከራይ ፡ ንግዱንም ፡ ቢተወው ፡ ወይም ፡ የሚሸጥበትና ፡ የሚገዛበት ፡ ቤት ፡ ቢከራይ ፡ ገንዘቡም ፡ ቢጠፋ ፡ ሊያጠቡት ፡ በኪ ራይ ፡ ስምምነት ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ ሕፃኑ ፡ ቢሞት ፡ ወይም ፡ አልጠባም ፡ ቢል ፡ ወይም ፡ ሴትዮዋ ፡ ማጥባቱን ፡ እንቢ ፡ ብትል ፡ ስምም ነቱ ፡ ይቀራል ።

፩ሺ፩፻፶፮ ክፍል ፡ የወገኖች ፡ ቁጥር ፡ አለበት ። ቀጣሪ ፡ ለተቀጣሪ ፡ በደመወዙ ፡ ልክ ፡ የተቀጠረበትን ፡ ሊሰጠው ፡ ይገባዋል ። ማብዛትና ፡ ማሳነስ ፡ ከተስማማ ፡ እንቢ ፡ እንዳይል ፡ እንደዚሁ ፡ ይሁን ። አንድ ፡ ሰው ፡ በረኃብ ፡ ምክንያት ፡ ስለገንዘብ ፡ ማናቸውንም ፡ ዋስ ፡ ቢጠራ ፡ ከዚ ህም ፡ በኋላ ፡ ቢበላ ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ጥጋብ ፡ ቢሆን ፡ ተመልሶ ፡ ያኖረውን ፡ ይቀበል ። በሁ ለተኛውም ፡ ዓመት ፡ ረኃብ ፡ ቢመጣ ፡ ደግሞ ፡ በውስጧ ፡ ይተው ።

፩ሺ፩፻፶፯ ከገንዘብ ፡ በማናቸውም ፡ የተዋሰ ፡ ሰው ፡ እጥፊ ፡ ከሆነው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መዓት ፡ የተነሣ ፡ በፍሬ ፡ ላይ ፡ በሚሆነው ፡ ዕዳ ፡ የለ በትም ። ዕዳ ፡ የሚገባውስ ፡ ከዚህ ፡ እማካይ ፡ በሆነ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ እንጂ ። ለሌላው ፡ በሚከ ፍለው ፡ ገንዘብ ፡ የተዋሰስ ፡ በትርፍ ፡ በኪሣ ራም ፡ ይከፍለው ፡ ዘንድ ፡ በአንድነት ፡ ገንዘብ፡ ዕዳ ፡ ይይዘዋል ። ተጠማኝ ፡ ከቀጠሮ ፡ ፍጻሜ ፡ በፊት ፡ ያለምክንያት ፡ እርስዋን ፡ የተጠመና ትን ፡ ቦታ ፡ ቢተዋት ፡ እስከ ፡ ቀጠሮ ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ በተከራይነቱ ፡ ይኖራል ። ባለተግባረ ፡ እድ ፡ እንዲሾም ፡ ስምምነት ፡ ቢሆን ፡ እኛ ፡ ለዚህ ፡ የደግ ፡ ሰው ፡ መሾምን ፡ እንሻለን ።

፩ሺ.፩፻፶፰ ወለእመ ፡ ተወሰበ ፡ ሰብእ ፡ መካነ ፡ ወእምዝ ፡ ተንሥኡ ፡ እስከ ፡ ሶድሜ ፡ ዓመታት ፡ ወኢያስተሐመሙ ፡ በዘይትፈቀድ ፡ ለመካን ፡ እምጠፈረ ፡ ጠፈር ፡ ወዘይመስሎ ፡ ወዝንቱ ፡ ብዉሕ ፡ ለዘመጽአ ፡ ላዕሌሁ ፡ በከመዝ ፡ ግብር ፡ ከመ ፡ ያብጽሕ ፡ በዘይቴ ፡ ሰብእ ፡ ወያስተጸንዕ ፡ በቅድሜሆሙ ፡ ዘተገብረ ፡ በዘየ ፡ ወእምዝ ፡ ይግበር ፡ ዘፈቀደ ፡፡ ወለእመ ፡ አንቀልቀለ ፡ መካን ፡ እምድልቅልቅ ፡ ሶዴሁ ፡ ለዝንቱ ፡ ላዕለ ፡ በዓለ ፡ መካን ፡፡

፩ሺ.፩፻፶፱ ወተዓስቦስ ፡ ይከውን ፡ እስከ ፡ ተፍጻሜተ ፡ ሕይወቱ ፡ ለተዓሳቢ ፡ አው ፡ እስከ ፡ ሶድሜ ፡ ዘተሰነአዉ ፡ ላዕሌሁ ፡ ሰብእ ፡ ተሰናእዎ ፡ ዘኢየዐዱ ፡ እም፲ ፡ ዓም ፡፡ ወኢይከውኖሙ ፡ ለሥዩማን ፡ ወለእሊአሆሙ ፡ ከመ ፡ ይትዐሰቡ ፡ አው ፡ ከመ ፡ የአኀዙ ፡ ምንተኒ ፡ እ ፡ ለርእሶሙ ፡ ወኢ ለካልአን ፡ ዘይትሜየጉ ፡ ቦቱ ፡ ዘእንበለ ፡ በተማይጦ ፡ በምሳሌ ፡ ወይንሥኡ ፡ ዘንተ ፡ እምእዴዊሆሙ ፡ ወይፈድዩ ፡ ሤጠ ፡ እምዮንቱ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜሁ ፡፡

፩ሺ.፩፻፷ ወዘኮነ ፡ አመክናተ ፡ ወዘይት ፡ ኢይደልዎ ፡ ከመ ፡ የሀብ ፡ ጸባሕተ ፡ ዘላዕሌሁ ፡፡ ወብዉሕ ፡ ከመ ፡ ይሚጥ ፡ ምንተኒ ፡ እምዓስበ ፡ ዚአሁ ፡ እምድኅረ ፡ ነገረ ፡ ለሊቀ ፡ ግብር ፡ ለሚጥ ፡ በቅድመ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ወዲያቆናት ፡ ወመኳንንት ፡ ካህናት ፡ ወምንባሬ ፡ ወንጉሥ ፡ አምላካዊ ፡ በቅድሜሆሙ ፡፡ ወለእመ ፡ ኢተከሥተ ፡ በህየ ፡ በካልእ ፡ ገጽ ፡ ዘይነሥኡ ፡ እምኔሁ ፡ ጸባሕተ ፡ ናሁ ፡ ብዉሕ ፡ ሚጠ ፡ ተዓስቦቱ ፡ በእደ ፡ መላኪ ፡ ዚአሁ ፡ ወእምዝ ፡ የሀብ ፡ ለጸባሕት ፡ ሚጠ ፡ ለዘተማየጦ ፡ ወይኩን ፡ ዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ በቅድመ ፡ ሰማዕት ፡፡



፩ሺ.፩፻፶፰ ሰዎች ፡ ቦታ ፡ ቢከራዩ ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ሶድሜ ፡ ቢታጡ ፡ ጠፈሩንና ፡ የመሰለውንም ፡ ከመሥራት ፡ ለቦታው ፡ በሚያስፈልገው ፡ ነገር ፡ ባይቶጉ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ለማመጣበት ፡ ሰው ፡ ደጋግ ፡ ሰዎች ፡ አምጥቶ ፡ ከዚያ ፡ የተደረገውን ፡ በፊታቸው ፡ ሊያጸና ፡ ይገባዋል ፡፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የወደደውን ፡ ያድርገው ፡፡ ከመንቀጥቀጥ የተነሣ ፡ ቦታው ፡ ቢነዋወጥ ፡ ዕዳው ፡ በባለቦታው ፡ ላይ ፡ ነው ፡፡

፩ሺ.፩፻፶፱ መከራየትስ ፡ እስከ ፡ ተከራዩ ፡ የሕይወት ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ ወይም ፡ ከ፲ ፡ ዓመት ፡ የማይበልጥ ፡ የውል ፡ ሰዎች ፡ እስከተስማሙበት ፡ ቀጠሮ ፡ ድረስ ፡ ይሆናል ፡፡ ለሹማምንትና ፡ ለሎሌ ዎቻቸውም ፡ ሊከራዩ ፡ ወይም ፡ ለራሳቸውና ፡ ለሌሎች ፡ በተመሳሳይ ፡ በመግዛት ፡ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የሚተነከሉበትን ፡ ማናቸውንም ፡ ሊይዙ ፡ አይገባቸውም ፡፡ ይህንንም ፡ ከእጃቸው ፡ ይቀበሉ ፡፡ ዋጋውንም ፡ ከመጀመሪያው ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ይክፈሉ ፡፡

፩ሺ.፩፻፷ ከታላላቆች ፡ ቦታዎች ፡ የሆነውም ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ግብር ፡ ሊሰጥ ፡ አይገባውም ፡፡ በኤጲስቆጶሳትና ፡ በዲያቆናት ፡ የክህነትም ፡ መዓርግ ፡ ባላቸው ፡ ሰዎች ፡ ፊት ፡ የዋጋዉን ፡ ሥራ ፡ (ልክ) ፡ ለዳኛ ፡ ከነገረ ፡ በኋላ ፡ ከሰብሉ ፡ ማናቸውንም ፡ ሊሸጥ ፡ መብት ፡ አለው ፡፡ እምላካዊ ፡ ወንጌልንም ፡ በፊታቸው ፡ ያስቀምጡ ፡፡ በዚያም ፡ በሌላ ፡ ዓይነት ፡ ከእርሱ ፡ ግብርን ፡ የሚቀበሉበት ፡ ባይገለጽ ፡ የመከራየቱ ፡ ዋጋ ፡ እነሆ ፡ ባለ ፡ ሀብቱ ፡ እጅ ፡ ይገባል ፡፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሸጠበትን ፡ ዋጋ ፡ ለግብር ፡ ይስጥ ፡፡ ይህም ፡ ሁሉ ፡ በምስክር ፡ ፊት ፡ ይሁን ፡፡

## አንቀጽ ፴ወ፰ቱ ፡፡

በእንተ ፡ ፍናዋት ፡ ወመራኅብት ፡ ወጸጉዓት ፡ ወሐድስ ፡ ሕንጻ ፡ ወምሕዋራት ፡ ማያት ፡ ውስተ ፡ ገራህት ፡ ወአፍላግ ፡ በድው ፡ ዘተናገረ እምአብትሊስ ፡፡

፩ሺ.፩፻፷፩ጠስ ፡ ፴ወ፰ቱ ፡ ክፍል ፡ በእንተ ፡ ፍትሐ ፡ ሕንጻ ፡ ዘባቲ ፡ ስቱፋን ፡፡ ወኢይደልዎ ፡ ለ፩ዱ ፡

## አንቀጽ ፡ ፴፰ ፡፡

ስለ ፡ ጎዳናዎችና ፡ ስለ ፡ አደባባዮች ፡ ስለ ፡ ሙቀላለፊያዎችና ፡ ስለሕንፃ ፡ ማደስ ፡ በእርሻም ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ውሀ ፡ መሂጃዎችና ፡ (ቦዮች) ፡ ስለምድረ ፡ በዳ ፡ ወንዞች ፡ ይናገራል ፡፡ ከአብትሊስ ፡ የተነገረ ፡ ነው ፡፡

፩ሺ.፩፻፷፩ ጠስ ፡ ፴፰ ፡፡ክፍል ፡ አንድነት ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ስላሉባት ፡ የሕንፃ ፡ ፍርድ ፡ ይናገራል ፡፡

እምእለ ፡ ይመልክዎሙ ፡ ለአብያተ ፡ ተሳትፎ ፡ ከመ ፡ ይሢም ፡ ላዕሌሆ ፡ ላዕካነ ፡ ዘእንበለ ፡ ምክረ ፡ እሊአሁ ።

፩ሺ፩፻፳፪ ወለሐጹርኒ ፡ ዘተሳትፎ ፡ ኢይደልዎ ፡ ለ፩ዱሂ ከመ ፡ ይንሥቶ ፡ አው ፡ ከመ ፡ ይሕንጾ ፡ ዘእን በለ ፡ በምክረ ፡ ሱታፌሁ ።

፩ሺ፩፻፳፫ ወኢይደልዎ ፡ ለ፩ዱሂ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ አቶነ ፡ አው ፡ ምንዳደ ፡ ብለኔ ፡ ኀበ ፡ ገቦ ፡ ሐጹር ፡ ዘተሳትፎ ፡ በዘይነክዮ ፡ እሳቱ ። ወለ እመ ፡ ገብረ ፡ ፩ዱ ፡ አቶነ ፡ ዘየዐርግ ፡ እምኔሁ ፡ ጢስ ፡ ዘይነክዮሙ ፡ ለእለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ ማኅደር ፡ ልዑልዊት ፡ ናሁ ፡ ይኤዝዝ ፡ ሕግ ፡ ከመ ፡ ይትከላእ ፡ እምፈንዎተ ፡ ጢስ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ለእመ ፡ ይከውን ፡ ሎቱ ፡ ርትዕ ፡ በእንተ ፡ ፈንዎቱ ።

፩ሺ፩፻፳፬ ወከማሁ ፡ ኢይደልዎሙ ፡ ለእለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ ማኅደር ፡ ልዑላዊት ፡ ከመ ፡ ይክዐዉ ፡ ማየ ፡ አው ፡ ከመ ፡ ይውግሩ ፡ እዳዋተ ፡ በዘየሐሥምዎሙ ፡ ቦቱ ፡ ለእለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስተ ፡ ዓፀድ ፡ ታሕታዊት ፡ አላ ፡ ይትከልኡ ፡ እምዝንቱ ። እስመ ፡ ይደልዎ ፡ ለኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ውስተ ፡ ማኅደሩ ፡ ዘኢያሐሥም ፡ ቦቱ እግዋሪሁ ፡ ወበከመ ፡ ዝንቱ ፡ ቃል ፡ ይደሉ ፡ በእንተ ፡ ዓዘቅት ።

፩ሺ፩፻፳፭ ወናሁ ፡ ይደልዎ ፡ ለ፩ዱ ፡ ከመ ፡ ይትክል ፡ ሰዋስወ ፡ በኀበ ፡ ገቦ ፡ አረፍት ፡ እሙር ፡ ለእመ ኮነ ፡ ውእቱ ፡ ዘኢይነኪ ፡ ካልአ ። ወመካንሰ ፡ ዕሩቅ ፡ ኢይደልዎ ፡ ለ፩ዱሂ ፡ ከመ ፡ ይክላእ ፡ እምአንሥኦቱ ፡ ወኢይሜኒ ፡ ከመ ፡ ይክልእ ፡ ፩ዱሂ ፡ ለኀረ ፡ ዚአሁ ፡ እምአርኅዎ ፡ አንቀጽ ፡ ዘይወስድ ፡ ኀበ ፡ ፍኖት ፡ ውሣጣይ ፡ እምኀበ ፡ ኢይነኪ ፡ ለኀላፍያን ።

፩ሺ፩፻፳፮ ክፍል ፡ በእንተ ፡ ፍትሐ ፡ ምጣኔ ፡ ማእከለ ፡ ሕንፃት ፡ ወአትክልት ። ወለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ብእሲ ፡ ከመ ፡ ይሕንጽ ፡ ቅጽረ ፡ ይረኀቅ ፡ እምቢጹ ፡ አሐተ ፡ ምሥጋረ ፡ እግር ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ቤት ፡ ሰብዓተ ፡ ምሥጋረ ፡ እግር ፡ ወለ እመ ፡ ኮነ ፡ ክርየት ፡ አው ፡ ግብ ፡ ይኩን ፡ በአምጣነ ፡ ዕመቆሙ ። ወለእመሰ ፡ ኮነ ፡ ዓዘቅት ፡ ፭ተ ፡ እመተ ፡ ለእመ ፡ ኢኮነ ፡ ዘአግዋሪሁ ፡ እምቀዲሙ ፡ ወይትገኃሥ ፡ እምዘ ፡ ከመዝ ፡ ግብር ።

፩ሺ፩፻፳፯ ወለእመ ፡ ኮነት ፡ ዕፀ ፡ ዘይት ፡ አው ፡ ዕፀ ፡



ያንድነት ፡ ቤት ፡ ካላቸው ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ ያለባልንጀሮቹ ፡ ምክር ፡ ጠባቂዎች ፡ ሊሾም ፡ አይገባውም ።

፩ሺ፩፻፳፪ ያንድነቱንም ፡ አጥር ፡ ያሰገደኛው ፡ (ሽሪኩ) ሊያፈርሰው ፡ ወይም ፡ ሊሠራው ፡ ለአንዱስ ፡ እንኳ ፡ አይገባውም ።

፩ሺ፩፻፳፫ ለአንድ ፡ ሰውስ ፡ እንኳ ፡ በአንድነቱ ፡ አጥር፡ አጠገብ ፡ እሳቱ ፡ በሚነካት ፡ ሁናቴ ፡ የማድ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ የውሽባ ፡ ቤት ፡ ሊሠራ ፡ አይገባ ውም ። አንድ ፡ ሰው ፡ በፎቅ ፡ ቤት ፡ የሚኖሩትን ፡ ሰዎች ፡ የሚነካቸው ፡ ጢስ ፡ ከእርሱ ፡ የሚወጣ፡ ማዕድ ፡ ቤት ፡ ቢሠራ ፡ ወደእነርሱ ፡ ጢስ ፡ ከመ ስደድ ፡ ይከለከል ፡ ዘንድ ፡ እነሆ ፡ ሕግ ፡ ያዝ ዛል ። ጢሱን ፡ ለመስደድ ፡ አግባብ ፡ ያለው ፡ ቢሆን ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፩ሺ፩፻፳፬ እንደዚሁም ፡ በፎቅ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ በምድር፡ ቤት ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ በሚያሳዝኗቸው ፡ ገን ዘብ ፡ ውሀ ፡ ሊያፈሱ ፡ ወይም ፡ ጥራጊ ፡ ሊጥሉ ፡ አይገባቸውም ። ከዚህ ፡ ይከልከሉ ፡ እንጂ ። ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ጐረቤቱን ፡ የማያሳዝንበትን ፡ በቤቱ ፡ ሊሠራ ፡ ይገባዋልና ። እንደዚሁም ፡ ነገር ፡ ስለጕድጓድ ፡ ይገባል ።

፩ሺ፩፻፳፭ እርሱ ፡ ሌላውን ፡ የማይጐዳ ፡ ከሆነ ፡ በታ ወቀ ፡ ቅጥር ፡ አጠገብ ፡ መሰላል ፡ ሊተክል ፡ ይገ ባዋል ። ቦታው ፡ ባዶ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ከማስረ ዘም ፡ ሊከለከል ፡ ለአንዱ ፡ አይገባውም ። አንድ ፡ ሰውስ ፡ እንኳ ፡ ጐረቤቱን ፡ ወደውስ ጠኛው ፡ መንገድ ፡ የሚወስድ ፡ በር ፡ ከመክ ፈት ፡ ሊከለከለው ፡ አይገባውም ። ለመንገደኞ ች ፡ የማይጐዳ ፡ ከሆነ ።

፩ሺ፩፻፳፮ ክፍል ። በሕንፃዎችና ፡ በተክሎች ፡ መካ ከል ፡ ስለመለካት ፡ ፍርድ ፡ ይናገራል ። አንድ ፡ ሰው ፡ ቅጽር ፡ ሊሠራ ፡ ቢወድ ፡ ከባልንጀ ራው ፡ ወሰን ፡ አንድ ፡ እርምጃ ፡ ይራቅ ። ቤት ፡ ቢሆን ፡ ፯ ፡ እርምጃ ፡ የወይን ፡ መጥመቂያ ፡ ወይም ፡ ጕድጓድ ፡ ቢሆን ፡ በጥልቀታቸው ፡ ልክ ፡ ይሁን ። የውሀ ፡ ጕድጓድ ፡ ቢሆን ፡ አስቀድሞ ፡ የጐረቤቱ ፡ ካልሆነ ፡ አምስት ፡ ክንድ ፡ ይሁን ። እንደዚህ ፡ ካለው ፡ ግብርም ፡ ይራቅ ።

፩ሺ፩፻፳፯ የዘይት ፡ ተክል ፡ ወይም ፡ የበለስ ፡ ተክል ፡

በለሰ ፡ ሁተ ፡ ምሥጋረ ፡ ይርኅቅ ፡ እምተክለ ፡ ካልኡ ፡ ወእምዝ ፡ ይትክል ። ወለእመሰ ፡ ኮነ ፡ እምካልእን ፡ ሰፀው ፡ ይኩን ፡ ፳ተ ፡ ምሥጋረ ፡ ወለእመ ፡ ኮነት ፡ ዖም ፡ ውስተ ፡ ማእከለ ፡ ዓፀደ ፡ ጎር ፡ ወሰፍሐ ፡ ሥረዊሃ ፡ እስከ ፡ መሠረቱ ፡ ለሐጹረ ፡ ካልኡ ፡ ወእሕሠም ፡ ይደልዎ ፡ ለሊቅ ፡ ከመ ፡ የአዝዝ ፡ መተሮቱ ።

፩ሺ፩፻፷፰ ወለእመ ፡ ኮኑ ፡ ፪ቱ ፡ አብያት ፡ ጽፉቃን ፡ ሰይኩን ፡ ማእከሌሆሙ ፡ ተራኅቆ ፡ መጠነ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ምኪያደ ፡ እግር ፡ ዘይትዌጠን ፡ ቦቱ ፡ እመሠረተ ፡ ሕንጻ ፡ እስከ ፡ ላዕሉ ፡ ዘዕዱ ፡ ዘላዊ ፡ ባሕቲቱ ፡ ወለእመ ፡ ኖኀ ፡ ሕንጻ ፡ እስከ ላዕሉ ፡ ይደልዎ ፡ ለዕዱ ፡ ከመ ፡ ያልዕል ፡ እስከ፡ ፍጻሜ ፡ ሕንጻ ፡ ወይግበር ፡ ቦቱ ፡ መስኮተ ፡ ሕንጻ ፡ ሐዲስ ፡ እው ፡ የሐድስ ፡ ዘበልየ ። ወለእመ ፡ ተኃሥሠ ፡ ዕዱ ፡ ብእሲ ፡ በስፍሐ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ መከየድ ፡ ኢይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይንሣእ ፡ ምሕዋጸ ፡ ኅሩ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘይኔጽር ፡ ኀበ ፡ ባሕር ፡ እመኮነ ፡ ብዙኅ ፡ እላ ፡ ይከውኖ ፡ ለውእቱ ፡ ከመ ፡ ይነጽር ፡ እንዘ ፡ ውእቱ ፡ ቅዉም ፡ ከመ ፡ ኢይትመየጥ ፡ እው ፡ ንቡር ፡ እስከ ፡ ኢያግብር ፡ ርእሶ ፡ ከመ ፡ ያቅድም ፡ ነጽሮተ ፡ ባሕር ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ማእከለ ፡ ፪ቱ ፡ ማኅደር ፡ ተራኅቆ ፡ መጠነ ፡ ፪ት ፡ ምኪያድ ፡ ይኩን ፡ ብዙኀ ፡ ዙሉ ፡ ዘይፈቅድ ፡ ከመ ፡ ይንሣእ ፡ ንጸሬ ፡ እምኔ ፡ ኅሩ ።

፩ሺ፩፻፷፱ ወዘየሐንጽ ፡ ማኅደረ ፡ እመ ፡ ኮነ ፡ ማእከሌሁ ፡ ወማእከለ ፡ ቢጹ ፡ ሰኩት ፡ እው ፡ መርኅብ ፡ ወማእከለ ፡ ሰኩት ፡ ወመርኅብ ፡ እመ ፡ ሀሎ ፡ ተራኅቆ ፡ መጠነ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ መከየድ ፡ ኢይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይወስኮ ፡ ለዕዱሂ ፡ ውስተ ፡ ማኅደሩ ። ወእመሰ ፡ ኮነ ፡ ርኂበ ፡ እምዝንቱ ፡ ኢይጸዓቁ ፡ እላ ፡ ይትዐቀቡ ፡ በበሥርዓታቲሆሙ ።

፩ሺ፩፻፸ ወለእመ ፡ ኮኑ ፡ ማኅደራት ፡ ፪ቱ ፡ ወኮነ ፡ ማእከሌሆሙ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ መከየድ ፡ ኢይወልጥ ፡ ዘንተ ፡ እምእርእያሁ ፡ ወኢያልዕል ፡ ማኅደሮ ፡ ወኢይግበር ፡ ውስቴቱ ፡ መሳክወ ። ወለእመ ፡ ሀለወ ፡ ማእከለ ፡ ፪ቱ ፡ ማኅደር ፡ ፲ቱ ፡ መከየድ ፡ ወእልቦ ፡ ዘእንበሌሃ ፡ ኢይደልዎ ፡ ለዳግማዊ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ መሳክወ ፡ ለንጻሬ ፡ ለእመ ፡ ኢኮነ ፡ ሎቱ ፡ ቅድመ ፡ እላ ፡ ይግበር ፡

ብትሆን ፡ ከሌላው ፡ ተክል ፡ ዘጠኝ ፡ እርምጃ ፡ ይራቅ ። ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ ይትከል ። ከሌሎች ፡ እንጨቶች ፡ ወገን ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ እምስት ፡ እርምጃ ፡ ይሁን ። ዛፍ ፡ በጎረቤት ፡ ቦታ ፡ መካከል ፡ ውስጥ ፡ ብትሆን ፡ ሥሯም ፡ እስከ ፡ ሊሳው ዐጥር ፡ መሠረት ፡ ድረስ ፡ ቢሰፋ ፡ ቢያሳዝነ ውም ፡ ዳኛ ፡ እንድትቈረጥ ፡ ሊያዝዝ ፡ ይገባ ዋል ።

፩ሺ፩፻፸፩ ሁለቱ ፡ ቤቶች ፡ የተጠጋጉ ፡ ቢሆኑ ፡ በመካከላቸው ፡ በዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ጫማ ፡ ልክ ፡ መራራቅ ፡ ይሁን ። ከሕንጻዉ ፡ መሠረት ፡ እስከ ፡ ላዩ ፡ ድረስ ፡ በእንድ ፡ መልክ ፡ የሚኖ መርበት ፡ ነው ። ሕንፃ ፡ እስከ ፡ ላይ ፡ ድረስ ፡ ቢረዝም ፡ ለእንዱም ፡ እስከ ፡ ሕንፃው ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ ሊያስረዝም ፡ አዲስ ፡ የሕንፃ ፡ መስኮት ፡ ሊሠራ ፡ ወይም ፡ ያረጀውን ፡ ሊያድስ ፡ ይገባዋል ። ፩ ፡ ሰው ፡ በ፲፪ ፡ ጫማ ፡ ስፋት ፡ ቢፈላለገው ፡ ከተፈቀደው ፡ ቦታ ፡ ሁኖ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ የሚያይ ፡ ከሆነ ፡ ጎረቤቱን ፡ መጉብኛ ፡ ሊከለክል ፡ አይገባውም ። እንዳይመለስ ፡ ቁሞ ፡ ይመለከት ፡ ዘንድ ፡ ወይም ፡ ተቀምጦ ፡ ባሕርን ፡ ለማየት ፡ ይጀምር ፡ ዘንድ ፡ ራሱን ፡ እስከማያዘልቅ ፡ ድረስ ፡ ለእርሱ ፡ ይገባዋል ፡ እንጂ ። በሁለቱ ፡ ቤቶች ፡ መካከል ፡ መጠ ፡ ጫማ ፡ ያህል ፡ ርቀት ፡ ቢሆን ፡ ከጎረቤቱ ፡ መተያየ ፡ ሊወስድ ፡ (ሊያወጣ) ፡ የሚወድ ፡ ሁሉ ፡ ባለመብት ፡ ይሁን ።

፩ሺ፩፻፸፪ ቤት ፡ የሚሠራ ፡ ሰው ፡ በእርሱና ፡ በጎረቤቱ፡ መካከል ፡ ወለል ፡ ወይም ፡ ሜዳ ፡ ቢኖር ፡ በወለሉና ፡ በሜዳው ፡ መካከል ፡ እሥራ ፡ ሁለት ፡ ጫማ ፡ ያህል ፡ ርቀት ፡ ቢኖር ፡ ለእንዱስ ፡ እንኳ ፡ ወደቤቱ ፡ ሊጨምረው ፡ አይገባውም ። ከዚህ ፡ የሰፋ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ በየወሰናቸው ፡ ይጠባበቁ ፡ እንጂ ፡ አይጨናነቁ ።

፩ሺ፩፻፸፫ ቤቶች ፡ ሁለት ፡ ቢሆኑ ፡ በመካከላቸው ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ጫማ ፡ ቢኖር ፡ ይህን ፡ ከመልኩ ፡ አያለውጥ ። ቤቱንም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አያድርግ ። በውስጡም ፡ መስኮቶች ፡ አያድርግ ። በሁለቱ ፡ ቤቶች ፡ መካከል ፡ ዐሥር ፡ ጫማ ፡ ቢኖር ፡ ከእርሰዋም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ባይኖር ፡ አስቀድሞ ፡ የነበረው ፡ ካልሆነ ፡ ለሁለተኛው ፡ ለመተያያ ፡ መስኮቶች ፡ ሊያደርግ ፡ አይገባውም ።

አንቀጽ ፡ ፵፯ ።

መሳክወ ፡ ለብርሃን ።

፩ሺ.፩፻.፸፩ ክፍል ፡ በእንተ ፡ ሐድሶ ፡ ሕንጻ ፡ ወማብረ ፡ ተልእኮ ፡ ወዘየሐንጽ ፡ ማኅደረ ፡ ዘወድቀ ፡ እመ ፡ ፈቀደ ፡ ከመ ፡ ያልዕል ፡ ኪያሁ ፡ እው ፡ ከመ ፡ ይሠውር ፡ እምነ ፡ ጎሩ ፡ ብርሃነ ፡ እው ፡ ይግበር ፡ ካልአ ፡ እምዝንቱ ፡ ለእእከዮተ ፡ ጎሩ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይዕቀብ ፡ ሥርዓተ ፡ ቤቱ ፡ ዘቀዳሚ ፡ ወኢይኅልፍ ፡ እምወሰኑ ።

፩ሺ.፩፻.፸፪ ወለዘሂ ፡ ኮነት ፡ ማኅደሩ ፡ በጽድቅ ፡ ዘባቲ ፡ መልእከተ ፡ ልዕልና ፡ ሥልጣን ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ያልዕላ ፡ ዘከመ ፡ ፈቀደ ፡ ኀበ ፡ ዘኢይኔነሥት ፡ ማኅደረ ፡ ካልኡ ፡ ዘታሕቴሁ ፡ ዘእንበለ ፡ በመልእከተ ፡ ተማህሎ ፡ ለኵሉ ፡ እብያት ፡ ለእመ ፡ እልባቲ ፡ መሳክው ፡ ለማኅደር ፡ ዘለንታሃ ። ወለእመ ፡ ኢኮነ ፡ ለከ ፡ ሥልጣን ፡ ከመ ፡ ታልዕል ፡ ማኅደረከ ፡ ከመ ፡ ኢይከላእ ፡ ብርሃነ ፡ ማኅደርየ ፡ ዘኮነ ፡ ያበውእ ፡ እመስኮተ ፡ እረፍትየ ፡ ወእምዝ ፡ ዘጋሕኩ ፡ እነ ፡ እረፍትየ ፡ ወመሳከውየ ፡ ወሊተ ፡ ዝንቱ ፡ መልእከት ፡ ላዕሌከ ፨ እው ፡ ኀተምክዋ ፡ መጠነ ፡ ፲ቱ ፡ ዓመት ፡ ወናሁ ፡ ተነሥተ ፡ ጽድቀ ፡ ተልእኮ ፡ እምእመ ፡ እልዐልኮ ፡ እንተ ፡ ለማኅደርከ ፡ እምድኅረ ፡ ዝንቱ ።

፩ሺ.፩፻.፸፫ ወለእመሰ ፡ ኢሐደስኮ ፡ እንተ ፡ በምንትኒ ፡ መልእከት ፡ ትተርፍ ፡ ሊተ ፡ በምግባሪ ፡ ወለእመ ፡ እርኀውኩ ፡ እነ ፡ መሳከውየ ፡ እምድኅረ ፡ ፲ቱ ፡ ዓመት ፡ እው ፡ ፳ ፡ ወሶበ ፡ ፈተድከ ፡ እንተ ፡ ከመ ፡ ትሕንጽ ፡ ይደልወኒ ፡ ከመ ፡ እከላእከ ፡ መካነ ፡ ዘምስሌየ ፡ በእንተ ፡ ዘሀሰወኒ ፡ ቃለ ፡ ጽድቅ ።

፩ሺ.፩፻.፸፬ ወእመ ፡ ኀደጋ ፡ ሊተ ፡ ለመልእከት ፡ ወእባሕከኒ ፡ ከመ ፡ እግበር ፡ ዕፀዋትየ ፡ ላዕለ ፡ ቤትከ፡ ወከብዶ ፡ ለእረፍትከ ፡ ወእመ ፡ ገደፍኩ ፡ ዘንተ ወሐነጽኩ ፡ ጽርሐ ፡ ወነሣእኩ ፡ ዓፀድየ ፡ ወነበርኩ ፡ ፲ተ ፡ ዓመተ ፡ ወኢያንበርኩ ፡ ዕፀዋትየ ፡ ውስተ ፡ መካኖሙ ። ወለእመ ፡ ኮንከ ፡ እንተኒ ፡ እምድኅረ ፡ ነሣእኩ ፡ ዓፀድየ ፡ ወነተምኩ ፡ መሳከውየ ፡ ወሐነጽከ ፡ እንተ ፡ መካነ ፡ ምስሌየ ፡ ወኀለፈ ፡ እምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ፲ቱ ፡ ዓመት ፡ ወናሁ ፡ ተፈጸመ ፡ ለከ ፡ ግዕዛን ።

፩ሺ.፩፻.፸፭ ወለእመ ፡ ኢሐደስካ ፡ በምንትኒ ፡ እላ ፡ ኀደጋ ፡ ኀበ ፡ ግብረ ፡ እስመ ፡ ጽድቀ ፡ ተል

ስለ ፡ መንገዶችና ፡ ስለ ፡ ቤት ፡ ሥራ ።

ለብርሃን ፡ መስኮቶች ፡ ያድርግ ፡ እንጂ ።

፩ሺ.፩፻.፸፩ ክፍል ። ሕንፃን ፡ ስለ ማደስና ፡ ስለ ፡ ተልእኮ ፡ (ቅድምና) ሥራ ፡ ይናገራል ። የወደቀ ፡ ቤት ፡ የሚሠራ ፡ ሰው ፡ ያንኑ ፡ ፎቅ ፡ (ደርብ) ፡ ሊያደርግ ፡ ወይም ፡ ከጎረቤቱ ፡ ብርሃንን ፡ ሊሠውር ፡ ወይም ፡ ጎረቤቱን ፡ ለማሳዘን ፡ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ሊሠራ ፡ ቢወድ ፡ የቀደመ ፡ የቤቱን ፡ ወሰን ፡ ሊጠብቅ ፡ ይገባዋል ። ከወሰኑም እይለፍ ።

፩ሺ.፩፻.፸፪ ቤቱ ፡ በእውነት ፡ የፎቅነት ፡ መልእክት ፡ (ቅድሚያ) ፡ ያላት ፡ ለሆነ ፡ ሰውም ፡ ከታች ፡ ያለው ፡ የጎረቤቱ ፡ ቤት ፡ እንዳይፈርስ ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡ ሊያስረዝማት ፡ ሥልጣን ፡ አለው ። ይኸውም ፡ ለቤቷ ፡ በሁሉም ፡ በኩል ፡ መስኮት ፡ ከሌላት ፡ ለቤቶች ፡ ሁሉ ፡ ከይቅርታ ፡ አገልግሎት ፡ በቀር ፡ ነው ። ከግድግዳዬ ፡ መስኮት ፡ የሚገባውን ፡ የቤቴን ፡ ብርሃን ፡ እንዳይከለክል ፡ ቤትህን ፡ ልታስረዝም ፡ ሥልጣን ፡ ባይኖርህ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ደጃፌንና ፡ መስኮቴን ፡ ብዘጋ ፡ ይህ ፡ መልእክት ፡ (ቅድሚያ) ፡ ከአንተ ፡ ይልቅ ፡ ለእኔ ፡ ነው ። ወይም ፡ ዐሥር፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ብዘጋት ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አንተ ፡ ቤትህን ፡ ብታስረዝመው ፡ እነሆ ፡ የተልእኮ ፡ (የቅድሚያ) ፡ ሰውነት ፡ ፈረሰ ።

፩ሺ.፩፻.፸፫ አንተ ፡ በማናቸውም ፡ ባታድሰው ፡ ውል ፡ (ቅድሚያ) ፡ በሥራዋ ፡ ለእኔ ፡ ትጸናለች ። ከሀሥር ፡ ወይም ፡ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ እኔ ፡ መስኮቴን ፡ ብከፍት ፡ አንተም ፡ ሕንፃ ፡ ልትሠራ ፡ ብትወድ ፡ የእውነት ፡ ቃል ፡ ስላለኝ ፡ ከእኔ ፡ ያለውን ፡ ቦታ ፡ ልከለክልህ ፡ ይገባኛል ።

፩ሺ.፩፻.፸፬ መልእከትን ፡ (ቅድሚያን) ፡ ለእኔ ፡ ብትተዋት ፡ ዕንጨቶቼንም ፡ በቤትህ ፡ ላይ ፡ እንዳደርግ ፡ ብትፈቅድልኝ ፡ ደጃፍህንም ፡ ቢከብደው፡ ይህን ፡ ትቼ ፡ ብሠራ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ቦታዬን ፡ ተቀብዬ ፡ ብኖር ፡ ዕንጨቶቼንም ፡ በቦታቸው ፡ ባላኖር ፡ አንተም ፡ እንዲህ ፡ ብትሆን ፡ ቦታዬን ፡ ተቀብዬ ፡ መስኮቴን ፡ ከደፈንሁ ፡ በኋላ ፡ አንተም ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ቤት ፡ ብትሠራ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ቢያልፍ ፡ እነሆ ፡ ነፃነት ፡ ላንተ ፡ ተፈጸመልህ ።

፩ሺ.፩፻.፸፭ በሥራዋ ፡ ተውካት ፡ እንጂ ፡ በማናቸውም ፡ ባታድሳት ፡ የቅድሚያ ፡ (የተልእኮ) ፡ አገባብ

እኮ ፡ ይተርፍ ፡ ሊተ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ። ወለ እመ ፡ ፈቀድኩ ፡ እምድኅረ ፡ ፳ ፡ ዓመት ፡ ክመ፡ እሚጥ ፡ ዕበውየ ፡ ኀበ ፡ ቅጽር ፡ ወእረስዮሙ ፡ ውስተ ፡ መካኖሙ ፡ እልቦ ፡ ዘይክልአኒ ፡ ክላእ. እምነ ፡ ዝንቱ ። ወውሳኔኒ ፡ ወእድያሞሙ ፡ ኢይሥርዑ ፡ በላዕሌሆሙ ፡ ክመ ፡ ይባእ ፡ ላዕ ሌሁ ፡ ፍድፋዴ ፡ ዘመን ፡ ነዊኅ ፡ ዘእንበለ ፡ ፴ ፡ ዓመት ።

፩ሺ፩፻፸፮ ወኢይደልዎ ፡ ለ፩ዱሂ ፡ ክመ ፡ ይግድፍ ፡ እዳዋተ ፡ ዲበ ፡ ቅጽር ፡ ዘኢኮነ ፡ ሎቱ ፡ ዳእሙ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ በላዕሌሁ ፡ እምሳለ ፡ ዝንቱ ፡ ትእ ዛዝ ፡ ወከማሁ ፡ ክመ ፡ ኢይዕርግ ፡ ጢስ ፡ እም እቶን ፡ ወእምቤተ ፡ ብስኔ ፡ ወከማሁ ፡ ውእቱ ፡ ጸታ ፡ ተልእኮ ።

፩ሺ፩፻፸፯ ወለእመ ፡ ፈተዱ ፡ በእንተ ፡ እሠንዮ ፡ ዓዘ ቅት ፡ ክመ ፡ ይዕርቅዎሙ ፡ ለመስተሳትፋን ፡ እለ ፡ ተበእሱ ፡ ለይውጥን ፡ ኵሉ ፡ ለለ፩ዱ ፡ በእንተ ፡ እሠንዮ ፡ ዝንቱ ፡ እመካኑ ፡ እስከ ፡ ይበጽሕ ፡ ኀበ ፡ መካነ ፡ ጎሩ ። ወለእመኒ ፡ እስ ተዋዕአ ፡ ፩ዱ ፡ እምስቱታፋን ፡ በእንተ ፡ ጥሪተ ፡ ተሳትፎ ፡ ወወሰነ ፡ ኪያሁ ፡ ይደልዎ ፡ ክመ ፡ ይትነሣእ ፡ ለካልኡ ፡ በዝንቱ ፡ በውእቱ ፡ ንዋይ ፡ ዘተዐውቀ ፡ እስከ ፡ ይነሥእ ፡ እምኔሁ ፡ ዘእስተዋዕአ ፡ እምንዋይ ።

፩ሺ፩፻፸፰ ወለእመ ፡ ጸነ ፡ ሐጹርከ ፡ ላዕለ ፡ ቤትየ ፡ መንፈቀ ፡ ስኩና ፡ እግር ፡ ይደልወኒ ፡ ክመ ፡ አሀብከ ፡ በዘይሜኒ ፡ ለሐኒጸታ ። ወዘእርኅወ ፡ መስኮተ ፡ በውስተ ፡ ሐጹር ፡ ዘኢኮነ ፡ ሎቱ ፡ ይደልዎ ፡ ክመ ፡ ያስተዋዕእ ፡ ላዕሌሁ ፡ እስከ ፡ ያገብእ ፡ ኀበ ፡ ህላዌሁ ።

፩ሺ፩፻፸፱ ክፍል ፡ በእንተ ፡ ማያት ፡ ወሰብአ ፡ እም ዳር ፡ ዘቈላ ፡ ወላዕሌሆሙ ፡ መልእክት ፡ ለእብ ያጽ ፡ ሎዓላውያን ፡ በግብር ፡ ዘይደልዎሙ ፡ ለእ ሠንዮተ ፡ ማያቲሆሙ ፡ ወሎሙ ፡ ተውላጠ ፡ ህየንተ ፡ ዝንቱ ፡ በቀኖት ፡ በንሚእቶሙ ፡ ተድላ ፡ ምድሮሙ ፡ ለእለ ፡ በላዕሉ ፡ ወሰብ ሐተ ፡ ዚአሃ ፡ ዘይከውን ።

፩ሺ፩፻፹ ወመልእክተ ፡ ማይሂ ፡ ለእመ ፡ ኮነት ፡ እምተ ንታ ፡ ትትገበር ፡ በዘመነ ፡ ሐጋይ ፡ ባሕቲቱ ፡ እው ፡ በ፩ዱ ፡ ወርኅ ፡ እው ፡ በዘይበዝኅ ፡ እም ወርኅ ፡ እው ፡ በዘይበዝኅ ፡ እም፩ዱ ፡ ዓመት ፡ ያዐርፅ ፡ ተገብሮቱ ፡ እምድኅረ ፡ ዘመን ፡ ውሱን ወከማሁ ፡ ፍኖትኒ ።



ነውና ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ለእኔ ፡ ይቀራል ፡ (ይጸናል) ። ከ፳ያ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ፅንጨቶ ቼን ፡ ወደቅጥር ፡ መልሼ ፡ በስፍራቸው ፡ ላደር ጋቸው ፡ ብወድ ፡ ከዚህ ፡ የሚከለክለኝ ፡ ክል ካይ ፡ የለም ። በወሰኑና ፡ በዙሪያቸውም ፡ ከ፴ ፡ ዘመን ፡ በቀር ፡ የረጅም ፡ ዘመን ፡ ብዛት ፡ በእ ርሱ ፡ ላይ ፡ እንዲገባ ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ አይ ወስኑ ።

፩ሺ፩፻፸፮ አንድ ፡ ሰው ፡ እንኳ ፡ የራሱ ፡ ባልሆነ ፡ ቅጥር ፡ ላይ ፡ ጥራጊውን ፡ ሊጥል ፡ አይገባውም። በእርሱ ፡ ላይ ፡ የዚህ ፡ ትእዛዝ ፡ አምሳያ ፡ ቢሆን ነው ፡ እንጂ ። እንደዚሁም ፡ ከማዕድ ፡ ቤትና ፡ ከውሽባ ፡ ቤት ፡ ጢስ ፡ እንዳይወጣ ፡ የአገልግ ሎትም ፡ (የቅድሚያ) ፡ ዓይነት ፡ እንዲሁ ፡ ነው።

፩ሺ፩፻፸፯ ስለውሀ ፡ ጉድጓድ ፡ የተጣሉትን ፡ አንድ ነት ፡ ያላቸውን ፡ ሰዎች ፡ ሊያስታርቋቸው ፡ ቢወዱ ፡ ሁሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ ከቦታው ፡ አን ስቶ ፡ ወደ ፡ ጐረቤቱ ፡ ቦታ ፡ እስኪደርስ ፡ ድረስ ፡ ይህን ፡ ለማሳመር ፡ ይጀምር ። አንድ ነት ፡ ካላቸው ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ ስላአንድነቱ ፡ ገንዘብ ፡ ቢያወጣጣ ፡ እርሱንም ፡ ቢወስን ፡ ከገ ንዘብ ፡ ያወጣውን ፡ ከእርሱ ፡ እስኪቀበል ፡ ድረስ ፡ በዚህ ፡ የታወቀውን ፡ ገንዘብ ፡ ሌላ ውን ፡ ሊጠይቀው ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ፩፻፸፰ እጥርህ ፡ በቤቴ ፡ ላይ ፡ ቢያዘነብል ፡ ለመ ሥሪያዋ ፡ በሚገባ ፡ የጫማ ፡ እኩሌታ ፡ ልሰ ጥህ ፡ ይገባኛል ። የእርሱ ፡ ባልሆነው ፡ እጥር ፡ መበኮት ፡ ያወጣ ፡ ሰው ፡ ወደጥንቱ ፡ እስኪመ ለስ ፡ ድረስ ፡ ለእርሱ ፡ ሊያወጣጣና ፡ ሊከፍል ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ፩፻፸፱ ክፍል ። ስለውሀዎችና ፡ ስለቆላ ፡ ምድር ፡ ሰዎች ፡ ይናገራል ። ለደገኞች ፡ ወንድሞች ፡ ውሀቸውን ፡ በማሳመር ፡ መስደድ ፡ በግድ ፡ የሚገባቸው ፡ ነው ። ለቆለኞችም ፡ የደገኞችን ፡ የምድር ፡ ተድላና ፡ የሆነውን ፡ ድልብዋን ፡ በመቀበላቸው ፡ ስለዚህ ፡ ጥቅም ፡ ፈንታ ፡ ለውጥ ፡ አለባቸው ።

፩ሺ፩፻፹ የውሀም ፡ ሕግ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ በበጋ ፡ ዘመን ፡ ብቻ ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ ወር ፡ ወይም ፡ ከወር ፡ በሚበዛ ፡ ወይም ፡ ካንድ ፡ ዓመት ፡ በሚ በዛ ፡ የምትሠራ ፡ ብትሆን ፡ ከተወሰነው ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ሥራው ፡ ይቆማል ። መንገድም፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። ይህ ፡ አንድ ፡ ዕለት ፡ ወይም ፡

ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዝንቱ ፡ ፩ደ ፡ ዕለተ ፡ እው ፡ እሐተ ፡ ሰዓተ ፡ እው ፡ ፩ደ ፡ መዐልተ ፡ እው ፡ እሐተ ፡ ሌሊተ ፡ ወትረ ፡ ይትፄጽል ፡ ተገብሮቱ ፡ በፍጻሜ ፡ ጊዜ ፡ ዘእሙር ፡ እስከ ፡ ይትገብእ ።

፩ሺ.፩፻፹፩ ወለእመ ፡ ነጽፈ ፡ ነቅዐ ፡ ማይ ፡ ዘይከውን ፡ ለ፩ዱሂ ፡ ከመ ፡ ይስሐብ ፡ እምኔሁ ፡ ዕድሜ ፡ ዓመታት ፡ ወእምዝ ፡ ገብአ ፡ ነቅዕ ፡ ወውኅዘ ፡ ናሁ ፡ ተሐደሰ ፡ ላዕሌሁ ፡ ከዊነ ፡ ተልእኮ ፡ ወገብእ ፡ ተሰሕቦተ ፡ ማይ ፡ እምኔሁ ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ ዘኮነ ፡ ቦቱ ፡ ቅድመ ።

፩ሺ.፩፻፹፪ ወለእመ ፡ እብሐከ ፡ ፩ዱሂ ፡ ከመ ፡ ታስተ ፡ እምዕቃለ ፡ ዚአሁ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ የሀብከ ፡ ፍኖተ ፡ በዘታስቲ ። ወለእመ ፡ ኢይትክሀለከ ፡ ከመ ፡ ትትገበሮ ፡ በካልእ ፡ ፍና ፡ ወዘቦቱ ፡ ተልእኮት ፡ ከመ ፡ ያስተ ፡ ወይርህዩ ፡ እንስሳሁ ፡ ውስተ ፡ ዓፀድከ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ሎቱ ፡ መልእክተ ፡ ካልእተ ፡ ወውእቱኒ ፡ ይግበር ፡ ልገተ ፡ በሀየ ።

፩ሺ.፩፻፹፫ ወዘቦቱ ፡ ምስቃይ ፡ በውስተ ፡ ምድረ ፡ ካልኡ ፡ ይደልዎ ፡ ለረኪበ ፡ ፍኖት ፡ ኀበ ፡ በዊእ ፡ ዘሎቱ ፡ ወቦኑ ፡ ያነብሩ ፡ መሬተ ፡ ወእእባነ ፡ ወንዋየ ፡ ተግባር ፡ ወኵሎ ፡ ዘይትፈቀድ ፡ ለሰቅየ ፡ ማይ ።

፩ሺ.፩፻፹፬ ወለእመኒ ፡ ኮነ ፡ ፈለግ ፡ ዘየኀልፍ ፡ ማእከለ ፡ ምድርየ ፡ ወምድርከ ፡ ወነሥእ ፡ እምነ ፡ ምድርከ ፡ በበንስቲት ፡ ወወሰኮ ፡ ውስተ ፡ ምድርየ ፡ እንዘ ፡ ኢተአምር ፡ ወእመ ፡ እኮ ፡ ትር እይ ፡ ሚ ፡ መጠነ ፡ ዘነሥእ ፡ ወበእይ ፡ መዋዕል ፡ ዝንቱ ፡ ዘኮነ ፡ እምነ ፡ ዘውኅዘ ፡ ውኂዝ ። ወለእመ ፡ ሰሐበ ፡ ሰሒበ ፡ ማእከሌነ ፡ እምሀገርከ ፡ ወወሰከ ፡ ቦቱ ፡ ውስተ ፡ ሀገርየ ፡ ወዝንቱ ፡ ይነብር ፡ ውስተ ፡ ግዝእትከ ።

፩ሺ.፩፻፹፭ ክፍል ፡ በእንተ ፡ ተሣይጦ ፡ ሕንፃ ። ወኵሉ ፡ ዘእኀዘ ፡ ወተሣየጠ ፡ ምድረ ፡ ወሐነፀ ፡ ውስቴታ ፡ እምድኅረ ፡ እእመረ ፡ ኪያሃ ፡ ከመ ፡ ይእቲ ፡ ኢኮነት ፡ ለዘይሠይጣ ፡ ሎቱ ፡ ኢይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይትነሣእ ፡ በእንተ ፡ ሣእሣእ ፡ እላ ፡ ያብሕዎ ፡ ለውእቱ ፡ ከመ ፡ ይንሥት ፡ ኪያሁ ፡ እምነ ፡ ምድር ፡ ወኢይንሥእዎ ፡ ለበዓለ ዚእሃ ፡ ምንተኒ ።

፩ሺ.፩፻፹፮ ወለእመ ፡ ጸንዐ ፡ ፩ዱሂ ፡ ወተሣየጠ ፡ ዓፀደ ፡ እንተ ፡ ኢኮነት ፡ ለሠያጢሃ ፡ ወሐረሰ ፡ ወሐነጸ ፡ በውስቴታ ፡ ይደልዎ ፡ ለመኰንን ፡ ከመ ፡

፩ ፡ ሰዓት ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ መዓልት ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ሌሊት ፡ ቢሆን ፡ በታወቀ ፡ የጊዜ ፡ ፍጻሜ ፡ እስኪመለስ ፡ ድረስ ፡ ዘወትር ፡ ሥራው ይቅር ።

፩ሺ.፩፻፹፩ ከእርሱ ፡ ይስብ ፡ ዘንድ ፡ ለአንዱ ፡ የሚሆነው ፡ የውሀ ፡ ምንጭ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ቢደርቅ ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ምንጩ ፡ ተመልሶ ፡ ቢፈስ ፡ እነሆ ፡ የአገልግሎት ፡ (የቅድሚያ) ፡ ሁኔታ ፡ ታደሰ ። የውሀውም ፡ ቦይ ፡ ከእርሱ ፡ ቀድሞ ፡ ወደነበረበት ፡ ቦታ ፡ ተመለሰ ።

፩ሺ.፩፻፹፪ አንድ ፡ ሰው ፡ ከምንጩ ፡ እንድትጠጣ ፡ ቢፈቅድልህ ፡ በምታጠጣ ፡ ገንዘብ ፡ መንገድ ፡ ሊሰጥህ ፡ ይገባዋል ። በሌላ ፡ መንገድ ፡ ልታጠጣ ባይቻልህ ፡ በእንተ ፡ ቦታ ፡ እንስሳውን ፡ ሊያጠጣና ፡ ሊያሰማራ ፡ መብት ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ለእርሱ ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ ይሥራ ፡ ዘንድ ፡ ይገባዋል ። ይኸውም ፡ ከዚያ ፡ ጎጆ ፡ (ቅልስ) ፡ ይሥራ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

፩ሺ.፩፻፹፫ በሌላው ፡ ምድር ፡ የውሀ ፡ ማጠጫ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ የእርሱ ፡ ወደ ፡ ሆነው ፡ መሬትና ፡ ድንጋይ ፡ የሥራ ፡ ዕቃም ፡ ውሀ ፡ ለማጠጣት ፡ የሚሻውን ፡ ሁሉ ፡ ወደሚያስቀምጡበት ፡ ለመግባት ፡ መንገድ ፡ ማግኘት ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ.፩፻፹፬ በምድሬና ፡ በምድርህ ፡ መካከል ፡ የሚያልፍ ፡ ወንዝ ፡ ቢሆን ፡ ከምድርህ ፡ በየጥቂቱ ፡ ወስዶ ፡ ሳታውቅ ፡ ወደኔ ፡ ምድር ፡ ቢጨምርም ፡ ባይሆን ፡ የወሰደው ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ከወረደው ፡ ጎርፍ ፡ የተነሣ ፡ ይህ ፡ የሆነው ፡ በመቼ ፡ ቀን ፡ እንደሆነ ፡ ብታውቅ ፡ በመካከላችን ፡ ያለው ፡ ውሀ ፡ ከአገርህ ፡ መሳብን ፡ ስቦ ፡ በአገሬ ፡ ውስጥ ፡ ቢጨምርበት ፡ ይህ ፡ በአንተ ፡ ግዛት ፡ ይኖራል ።

፩ሺ.፩፻፹፭ ክፍል ። ሕንፃን ፡ ስለመግዛት ፡ ይናገራል ። ምድር ፡ ገዝቶ ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እርሷ ፡ ለሸጠለት ፡ ሰው ፡ እንዳልሆነች ፡ እርሷን ፡ ካወቀ ፡ በኋላ ፡ ቤት ፡ ቢሠራባት ፡ ስለገንዘቡ ፡ ሊፈላለግ ፡ አይገባውም ። ከምድር ፡ እርሱን ፡ ያፈርስ ፡ ዘንድ ፡ ያስናብቱት ፡ እንጂ ። ባለቤቷንም ፡ አንዳች ፡ አይከልከሉት ።

፩ሺ.፩፻፹፮ አንድ ፡ ሰው ፡ የሻጭ ፡ ገንዘብ ፡ ያልሆነውን ፡ ቦታ ፡ ጨክኖ ፡ ቢገዛ ፡ በውስጧም ፡ ቢዘራና ፡ ቤት ፡ ቢሠራ ፡ ለባለቦታው ፡ በውነት ፡ የሚ

አ.ይ.ምትር ፡ ፍትሐ ፡ እስከ ፡ ይኤጽር ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ለበዓለ ፡ ዓፀድ ፡ ዘበእማን ፡ ይደልዎ ፡ ወዘኮነ ፡ ዘሀለዎ ፡ ከመ ፡ ይሕንጽ ፡ ውስቴታ ፡ ይእቲ ፡ ሕንጻ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ የሀብ ፡ ሣእሣአ ፡ ዘተሐደሰ ፡ ቦቱ ፡ ሕንጸ ፡ ወእምዝ ፡ ይንሥኦ ፡ ለዓፀዱ ፡ ወዘተወሰከ ፡ ውስቴታ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ነዳየ ፡ ዘኢኀረየ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ዘተገብረ ፡ ለይንሣእ ፡ ዘተአመነ ፡ ወዘሐነጸ ፡ ሕንጸሁ ፡ ወባሕቱ ፡ ይቅልል ፡ ለበዓለ ፡ ዓፀድ ፡ ከመ ፡ የሀብ ፡ እምሣእሣኡ ፡ በእንተ ፡ ዘተሐደሰ ፡ በዘ ተሰንአወ ፡ ቦቱ ፡ ወይንሣእ ፡ ኪ.ያሁ ።

፩ሺ፩፻፺፯ ወእመኒ ፡ በዓለ ፡ ዓፀድ ፡ አርአየ ፡ ቅድመ ፡ ከዊን ፡ ተማይጦታ ፡ ኢይደልዎ ፡ ከመ ፡ ያማ ብእ ፡ በግብር ፡ እመኒ ፡ ኮነ ፡ ነዳየ ፡ አላ ፡ ይደ ልዎ ፡ ከመ ፡ ይንሣእ ፡ ዓሥበ ፡ ዘአሃ ፡ እምድ ኅረ ፡ ተሐድሶታ ፡ ወይትኀለቍ ፡ ሳዕሌሁ ፡ ኵሉ ሣእሣአ ፡ ዘተሐደሰ ፡ ቦቱ ።

፩ሺ፩፻፺፰ ወለእመ ፡ ኀብአ ፡ ዕዳሁ ፡ ማኅፀንተ ፡ ዘአሁ ዘአማኅፀንዎ ፡ ወሤጦ ፡ አው ፡ ወሀበ ፡ ኪያሃ ፡ ወአእመረ ፡ ዘንተ ፡ ለበዓለ ፡ ማኅፀንት ፡ ፍቁሩ ፡ ወኢነበረ ፡ ለዘተሣየጠ ፡ ወወሀበ ፡ ሎቱ ። አው ፡ ወሀበ ፡ ፍኖተ ፡ ካልእተ ፡ በዕድሜ ፡ ፲ቱ ፡ ዓመት ፡ ለዘሀለወ ፡ ወለዘኢሀሎ ፡ እስከ ፡ ይመ ጽእ ፡ እምንግደቱ ፡ ፳ ፡ ዓመት ፡ ናሁ ፡ ይጸንስ ፡ ምልክናሁ ፡ ለዘኮነ ፡ ኀቤሁ ፡ እምድኅረ ፡ ፲ ፡ ዓመት ፡ ወመላኪሁሰ ፡ ዘበእማን ፡ ለእመ ፡ ኢያእመረ ፡ ዘንተ ፡ ኢይጸንስ ፡ ለዘኮነ ፡ ኀቤሁ ፡ ዘእንበለ ፡ እምድኅረ ፡ ፴ ፡ ዓመት ። ለእመ ፡ አጠየቀ ፡ ወይብል ፡ ዘዚአየ ፡ በ፲ቱ ፡ ዓመት ፡ አው ፡ በ፳ ፡ አው ፡ እስከ ፡ ፴ ፡ ድልው ፡ ሎቱ ፡ ኢይንሥእዎ ፡ በምንትኒ ፡ ሀገር ፡ ዘተ ንት ፡ አው ፡ ገራህቶ ፡ አው ፡ ርስቶ ፡ ይደልዎሙ ከመ ፡ ኢይክልእዎ ፡ ኀበ ፡ ገቢአ ፡ ርስቱ ፡ ዘሢ ፡ ተሣየጠ ፡ ኢይክልአ ።

፩ሺ፩፻፺፱ ወንዋይ ፡ ዘይትወሐስ ፡ ለእመ ፡ ነበረ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ አሐዱ ፡ ፴ ፡ ዓመተ ፡ ወኢሰበከ ፡ በእንቲአሁ ፡ በምንትኒ ፡ እስመ ፡ ኮነ ፡ ንዋ ፡ መለኮ ። ወለእመ ፡ ሚጥኮ ፡ መክፈልተ ፡ ሀገ ርየ ፡ ወተካየድኮ ፡ ከመ ፡ ይሑር ፡ ውስቴታ ፡ ማይ ፡ ወቦአ ፡ ስለተ ፡ ሰይሜ ፡ ዘይዌስኖ ፡



ገባው ፡ እንደሆነ ፡ እስኪያይ ፡ ድረስ ፡ ፍርድ ፡ እንዳይቆርጥ ፡ ለዳኛ ፡ ይገባዋል ። ይችን ፡ ሕንፃ ፡ በውስጧ ፡ ሊሠራ ፡ ፈቃድ ፡ ያለው ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ሕንፃው ፡ የታደሰበትን ፡ ገንዘብ ፡ ሊሰጥ ፡ ይገባዋል ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ቦታው ንና ፡ በውስጧም ፡ የተጨመረውን ፡ ይውሰድ ። የተገመተውን ፡ ለማድረግ ፡ የማይወድ ፡ ድሀ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ የታመነውንና ፡ የሥራውን ፡ ሕንፃ ፡ ይውሰድ ። ነገር ፡ ግን ፡ ስለማደሻው ፡ በተስማማበት ፡ ገንዘብ ፡ ከገንዘቡ ፡ ይስጠው ፡ ዘንድ ፡ ለባለቦታው ፡ ያቅልል ። እርሱንም ፡ ይቀበል ።

፩ሺ፩፻፺፯ ባለቦታው ፡ አስቀድሞ ፡ የመሸጥን ፡ ሁኔታ፡ ቢያሳይ ፡ ምንም ፡ ድሀ ፡ ቢሆን ፡ በግድ ፡ ሊመ ልሰበት ፡ አይገባውም ። ከመታደሷ ፡ በኋላ ፡ ዋጋዋን ፡ ሊቀበል ፡ ይገባዋል ፡ እንጂ ። የታደሰ በትንም ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ይቍ ጠር ።

፩ሺ፩፻፺፰ አንዱም ፡ ያስጠበቁትን ፡ አደራውን ፡ ሰውሮ ፡ ቢሸጣት ፡ ወይም ፡ እርሷን ፡ አሳልፎ ፡ ቢሰጣት ፡ የባለአደራ ፡ ወዳጁም ፡ ይሁን ፡ ቢያ ውቅና ፡ ለገዥው ፡ ባይነግረው ፡ ለእርሱም ፡ ቢሰ ጠው ፡ ለአለ ፡ ሰው ፡ በዓሥር ፡ ዓመት ፡ ለሌ ለም ፡ ከመንገዱ ፡ እስኪመለስ ፡ ድረስ ፡ በኻያ ፡ ዓመት ፡ ቀጠሮ ፡ ሌላ ፡ መንገድ ፡ (ምክንያት) ፡ ቢሰጠው ፡ ከ፴ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ የሆነው ፡ እጅነቱ ፡ እነሆ ፡ ይጸናል ። ዕውነተኛ ፡ ባለቤቱ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ባያውቅ ፡ ከ፴ዘመን ፡ በኋላ ፡ ካልሆነው ፡ በቀር ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ለሆነው ፡ አይጸናለትም ። በ፲ ፡ ዓመት ፡ ወይም ፡ በኻያ ፡ ዓመት ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ፴ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ የእኔ ፡ ገንዘብ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ቢናገር ፡ ይገባዋል ። በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ የጥንት ፡ ሀገሩን ፡ ወይም ፡ እርሻውን ፡ ወይም ፡ ርስቱን ፡ አይውሰዱበት ። ወደርስቱ ፡ ከመግ ባት ፡ እንዳይከለክሉት ፡ ይገባቸዋል ። የገዛም ፡ አይከልክለው ።

፩ሺ፩፻፺፱ በውስት ፡ የሄደ ፡ ገንዘብ ፡ በአንድ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ፴ ፡ ዓመት ፡ ቢኖር ፡ በማናቸውም ፡ ስለ እርሱ ፡ ባይናገር ፡ እነሆ ፡ ገንዘቡ ፡ ነው ፡ እኮ ። ከሀገሬ ፡ ድርሻዬን ፡ ብሸጥ ፡ በውስጧም ፡ ውሀ ፡ እንዲሄድ ፡ ብዋዋል ፡ ማጠጣቷን ፡ ከማ ድረጌ ፡ አስቀድሞ ፡ ሕግ ፡ የወሰነው ፡ የቀጠሮ ፡

ሕግ ፡ እምቅድመ ፡ ንበርትየ ፡ ስትዩታ ፡ እስመ ድሉት ፡ ሊተ ፡ እምድኅረ ፡ ቀዊም ፡ ወለእመ ፡ ነበርክሙ ፡ ወኢእንለዓክ ፡ ውስቴታ ፡ ማየ ፡ ተበርዐ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ መላኪ ፡ ቀዳሚ ፡ ኢይከውኖ ፡ ከመ ፡ ይክላእ ፡ እምኀሊፈ ፡ ማይ ፡ ወከማሁ ፡ ተማየጠ ፡ ኢይከውኖ ፡ ከመ ፡ ይክላእ ፡ እስመ ፡ ተማየጠ ፡ ወሡምረ ፡ በዛቲ ፡ ክበዳት ።

፩ሺ.፩፻ ፺ ክፍል ፡ በእንተ ፡ ፍናው ፡ ሐጸራ ፡ ለፍኖት ፡ ሕዕርት ፡ እምነ ፡ ቀኖናት ፡ ኵሉ ፡ ዘንበር ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ አንቀጽ ። ኢየሐድስ ፡ ፩ዱሂ ፡ ምንተኒ ፡ ዘይመጽእ ፡ እምኔሁ ፡ ንከዮተ ፡ ካልእ ፡ ወኵሉ ፡ ድልወት ፡ ዘኢይትገበር ፡ ዘይደልዎ ፡ መጠነ ፡ ፲ቱ ፡ ዓመት ፡ ወዝንቱ ፡ ለሀልዋን ፡ ወ፳ ፡ ዓመት ፡ ለነጋድያን ፡ ተበርዐ ፡ ዘእንበለ ፡ ፍኖተ መቃብር ፡ እስመ ፡ ለያእቲ ፡ ኢያበርዓ ፡ ርሕቅና ፡ ዘመን ። ወዝንቱ ፡ ዕድሜ ፡ ተራከቦቱ ፡ ለሙቴሕ ፡ እስከ ፡ ግብእቱ ፡ ወለእብድኒ ፡ እሙ ፡ ለዘያበርዖ ፡ ደዌ ፡ እስከ ፡ ተፈውሶቱ ፡ ወዘበጽሐ ፡ ላዕለ ፡ አበሳ ፡ ኢያንጕንዶ ፡ ዘመን ፡ እምዘ ፡ ይደልዎ ። ወዘሎቱ ፡ ድልወት ፡ ሎቱ ፡ ኵሉ ፡ ዘኢይትፌጸም ፡ ዝንቱ ፡ ድልወት ፡ ዘእንበሌሁ ።

፩ሺ.፩፻ ፺፩ ወኢይደልዎ ፡ ለመኑሂ ፡ ከመ ፡ ያማስን ፡ መርኅበ ፡ ሀገር ፡ ወጽጕንቲሃ ፡ ወዘንተብሬ ፡ ዘንተ ፡ ይደልዎ ፡ አግብእቶሙ ። ወይኩን ፡ ስፍሐ ፡ ምጣኔ ፡ ማእከለ ፡ ቤት ፡ ወቤት ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ መክየድ ፡ እምላዕል ፡ እስከ ፡ መትሕት ፡ ወኢይደልዎ ፡ ለ፩ዱሂ ፡ ከመ ፡ ይክላእ ፡ ለጎሩ ፡ ሐውጾተ ፡ ባሕር ፡ በእለይንቲሁ ፡ ዘእንበለ ፡ ይኩን ፡ ማእከለ ፡ ፪ቱ ፡ አብያት ፡ መጠነ ፡ ፪ት ፡ ምክያድ ።

፩ሺ.፩፻ ፺፪ ወኵሉ ፡ ዘፈቀደ ፡ ከመ ፡ ይሕንጽ ፡ ሐጹረ ፡ ይርሐቅ ፡ እምቤጹ ፡ ፩ደ ፡ ምሥጋረ ፡ ወእመሰ ፡ ኮነት ፡ ቤት ፡ ፪ተ ፡ ምሥጋረ ፡ ወእመ ፡ ኮነ ፡ ምክያድ ፡ እው ፡ ግብ ፡ ይኩን ፡ በእምጣነ ፡ ዕመቆሙ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ፳ቱ ፡ እመት ፡ ወማእከለ ፡ ዘይትስ ፡ ወበለስ ፡ ፱ቱ ፡ ምሥጋር ፡ ወዘተርፉስ ፡ ዕበዋት ፡ ፳ቱ ፡ ምሥጋር ።



ቀን ፡ ቢደርስ ፡ ከጸና ፡ በኋላ ፡ ለእኔ ፡ ነውና ፡ ይገባኛል ። ብሠራት ፡ በውስጧም ፡ ውሀ ፡ ባስተላልፍባት ፡ ውሉ ፡ ተሻረ ። ባለቤቱ ፡ ቀዳሚ ፡ ቢሆን ፡ ውሀ ፡ ከማሳለፍ ፡ ሊከለክል ፡ አይገባውም ። በዚች ፡ ውል ፡ ወድዶ ፡ ገዝቷልና ።

፩ሺ.፩፻ ፺ ክፍል ። ስለታጠረች ፡ መንገድ ፡ ስለእጥሯ ፡ ዓይነት ፡ ይናገራል ። ከመጻሕፍት ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ የተጻፈ ፡ ነው ። አንዱም ፡ ከእርሱ ፡ የተነሣ ፡ የጎረቤቱ ፡ መጎዳት ፡ የሚመጣበትን ፡ ማናቸውንም ፡ አያድስ ። የሚገባውን ፡ የማይሠራበት ፡ አግባብ ፡ ሁሉ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ያህል ፡ ነው ። ይህም ፡ ለእሉት ፡ ነው ። ስመንገደኞችም ፡ እሩቅ ፡ አገር ፡ ለሄዱት ፡ ግን ፡ ኻያ ፡ ዓመት ፡ ነው ። ከመቃብር ፡ መንገድ ፡ በቀር ፡ ይቀራል። ይኸን ፡ የዘመን ፡ ርሀቀት ፡ አያስቀራትምና ። ይኸውም ፡ የታሰረ ፡ ሰው ፡ እስኪመለስ ፡ ድረስ ፡ የመገናኛ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። እእምሮውን ፡ ያጣ ፡ ወይም ፡ ደዌ ፡ ሥራ ፡ ፈት ፡ ያደረገው ፡ እስኪድን ፡ ድረስ ፡ ነው ። ከበደል ፡ ላይ ፡ የደረሰውን ፡ ሰው ፡ ከሚገባው ፡ ዘመን ፡ አያዘገየውም ። አግባብ ፡ ለእርሱ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ አግባብ ፡ ያለእርሱ ፡ የማይፈጸምለት ፡ ነው ።

፩ሺ.፩፻ ፺፩ የአገሩን ፡ ሜዳና ፡ መተላለፊያዎቿን ፡ ሊያጠፋ ፡ ለማንም ፡ አይገባውም ፡ ይህን ፡ ያደረገም ፡ ሊመልባቸው ፡ ይገባዋል ። በቤትና ፡ በቤት ፡ መካከል ፡ የልኩ ፡ ስፋት ፡ ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ ፲፪ ፡ ጫማ ፡ ይሁን ። ባሕሩን ፡ በዓይኑ ፡ ከማየት ፡ ጎረቤቱን ፡ ይከለክለው ፡ ዘንድ ፡ ለአንድ ፡ ሰው ፡ እንኳ ፡ አይገባውም ። በሁለት ፡ ቤቶች ፡ መካከል ፡ መቶ ፡ ጫማ ፡ ያህል ፡ ቢኖር ነው ፡ እንጂ ።

፩ሺ.፩፻ ፺፪ አጥር ፡ ሊያጥር ፡ የወደደ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከባልንጀራው ፡ አንድ ፡ እርምጃ ፡ ይራቅ ። ቤት ፡ ብትሆን ፡ ግን ፡ ስባት ፡ እርምጃ ፡ የወይን ፡ መጥመቂያ ፡ ወይም ፡ ጉድጓድ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ በጥልቀታቸው ፡ ልክ ፡ ይሁን ። የውሀ ፡ ጉድጓድ ፡ ቢሆንም ፡ ፳ ፡ ክንድ ፡ በዘይትና ፡ በበለስ ፡ መካከል ፡ ግን ፡ ፱ ፡ እርምጃ ፡ ይሁን ። በቀሩት ፡ እንጨቶች ፡ ግን ፡ ፳ ፡ እርምጃ ።

## አንቀጽ ፡ ፴፯ ።

፩ሺ.፩፻ ፺፫ ወተንሥሣተ ፡ ውሳኔያት ፡ ይደልዎሙ ፡ ለፈ ታሕያን ፡ ከመ ፡ ይሕትቱ ፡ መጽሐፈ ፡ ታሪኮሙ ወእምነ ፡ ዘሀሎ ፡ ከሠተ ፡ ወዘልማድ ። ወእመሰ ፡ ፍኖት ፡ እምርት ፡ እምጽአተ ፡ ድልቅልቅ ፡ እው ፡ እምርደተ ፡ ማይ ፡ እው ፡ ዘይመስሎ ፡ ለዝንቱ ፡ ይደልዎ ፡ ለገዛኢ ፡ ቅሩብ ፡ ከመ ፡ ያሚጣ ፡ ኀበ ፡ ዘኮነት ፡ ቦቱ ፡ ውስተ ፡ ምድሩ ። ወለዓዘቅተ ፡ ተሳትፎስ ፡ ይደልዎ ፡ ለኵሉ ፡ ለለ ፩ዱ ፡ አሠንዮታ ፡ በዘይደሉ ፡ ወዘየሐንጽ ፡ ማኅደረ ፡ ብሊተ ፡ ኢይትዐደ ፡ እምወሰና ፡ ዘተዳሚ ፡ ወኢይከላእ ፡ እምኅሩ ፡ ነጽሮ ፡ ብርሃን ፡ ወኢነጽሮተ ፡ ባሕር ፡ ዘእንበለ ፡ በተሰናአዎ ።

፩ሺ.፩፻ ፺፬ ክፍል ፡ ዘተወሰከ ፡ እምዘተነግረ ፡ በአብጥሊስ ፡ ዘፍትሐ ፡ ምጣኔ ። ዘያነብር ፡ በፍኖት ፡ ምንተኒ ፡ ዘይከውን ፡ ለአሕሥሞ ፡ ይደሉ ፡ ለዳ ፡ ላዕሌሁ ፡ በዘገብረ ፡ ወፈድየ ፡ ኵሉ ፡ ለዳ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ግብር ፡ ኵለንታሁ ፡ ባሕቲቱ ፡ ዘገብረ ። ወእመሰ ፡ ኮነ ፡ መንፈቀ ፡ ገቢር ፡ ይኩን ፡ ዕዳሁ ፡ በመንፈቁ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ካልእ ፡ ዘአገበሮ ፡ ለገቢረ ፡ ዝንቱ ፡ ግብር ፡ ኢይደልዎ ፡ ዕዳ ። ወከማሁ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘአገብሮ ፡ ገባሪሃ ፡ ለአሕሥሞ ፡ ወተካየደ ፡ በዘየ ፡ ወእምዝ ፡ ተከልአ ፡ ኢይደልዎ ፡ ዕዳ ፡ ወከማሁ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ገብረ ፡ ዘንተ ፡ በምልክና ፡ ዚአሁ ።

፩ሺ.፩፻ ፺፭ ወለእመ ፡ ጸነ ፡ አረፍት ፡ መንገለ ፡ ፍኖት ፡ ወሰአልዎ ፡ ለበዓለ ፡ ዚአሁ ፡ ከመ ፡ ይንሥቶ ፡ ወአስምዑ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወኢነሠቶ ፡ በብዙኅ ፡ ዕድሜ ፡ እንዘ ፡ ይትከሀሎ ፡ ለነሢቶቱ ፡ ይደልዎ ፡ ዕዳሁ ፡ ለዘጠፍአ ፡ በድቀተ ፡ ዚአሁ ፡ እመሂ ፡ ነፍስ ፡ ወእመሂ ፡ ንዋይ ፡ ወእመሂ ፡ ኮነ ፡ ጽንቱ ፡ መንገለ ፡ ሐጼር ፡ ይትኃሠሥ ፡ በነሢቶቱ ፡ መላኬ ፡ ሐጼር ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ አረፍት ፡ ዘተሳትፎ ፡ ማእከለ ፡ ፫ቱ ፡ ይደልዎ ፡ ፈድዮ ፡ ሣልስተ ፡ እዴሁ ፡ ለዘጠፍአ ፡ ወዝንቱ ኵሉ ፡ ለእመ ፡ ኢተከልአ ፡ እምዘ ፡ ሥሉጥ ፡ ከመ ፡ ኢይንሥትዎ ።

፩ሺ.፩፻ ፺፮ ክፍል ፡ ዘይትልዎ ፡ ለዘተነግረ ፡ በዝንቱ ፡ አንቀጽ ። ወምድርኒ ፡ እንተ ፡ ኢትበቍዕ ፡ በእንተ ፡ ተከልአተ ፡ ማይ ፡ እምኔሃ ፡ እው ፡ ተኀይሎተ ፡ ማይ ፡ ላዕሌሃ ፡ ወኢይሰማዕ ፡ እምኔሁ ፡ ቃል ፡ በእንተ ፡ ተሐንጾታ ፡ እለ ፡ ውስተ ፡

## ስለ ፡ መንገዶችና ፡ ስለ ፡ ቤት ፡ ሥራ ።

፩ሺ.፩፻ ፺፫ ስለውሳኔዎች ፡ ምርመራም ፡ የታሪካቸውን ፡ መጽሐፍ ፡ በግልጽ ፡ ካለውና ፡ ከልማድም ፡ ይመረምሩ ፡ ዘንድ ፡ ለዳኞች ፡ ይገባቸዋል ። የታወቀችው ፡ ጐዳና ፡ ከመነዋወጥ ፡ መምጣት ፡ ወይም ፡ ከውሀ ፡ መውረድ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ ከመሰለው ፡ የተነሣ ፡ ከተበላሸ ፡ በምድሩ ፡ ውስጥ ፡ ወደነበረችበት ፡ ሊመልሳት ፡ በቅርብ ፡ ላለው ፡ ባለቤት ፡ ይገባዋል ። ያንድነቱን ፡ የውሀ ፡ ጕድጓድ ፡ ሁሉም ፡ ለእያንዳንዱ ፡ በሚገባ ፡ ሊያሳምሩት ፡ ይገባዋል ። ያረጀችውን ፡ ቤት ፡ የሚሠራ ፡ ሰው ፡ ከጥንት ፡ ወሰኗ ፡ አይለፍ ፡ በመስማማት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ብርሃን ፡ ከማየት ፡ ጐረቤቱን ፡ አይከልክል ።

፩ሺ.፩፻ ፺፬ ክፍል ። የልኩ ፡ ፍርድ ፡ በአብጥሊስ ፡ ከተነገረው ፡ የተጨመረ ፡ ነው ። ለጕዳት ፡ የሚሆነውን ፡ ማናቸውንም ፡ በጎዳና ፡ የሚያኖር ፡ ሰው ፡ ባደረገው ፡ ላይ ፡ ዕዳ ፡ ይገባዋል ፤ ሥራውን ፡ ሁሉ ፡ ብቻውን ፡ የሠራው ፡ ቢሆን ፡ ዕዳውን ፡ ሁሉ ፡ መክፈል ፡ ይገባዋል ። እኩሌታውን ፡ የሠራው ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ዕዳው ፡ በግማሽ ፡ ይሁን ። ይህን ፡ ሥራ ፡ ለመሥራት ፡ ያስገደደው ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ዕዳ ፡ አይገባውም ። እንደዚሁም ፡ ጥፋት ፡ አድራጊው ፡ ያስገደደው ፡ ቢሆን ፡ በዚያም ፡ ቢማማል ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ቢከለከል ፡ ዕዳ ፡ አይገባውም ። ይህንም ፡ በግዛቱ ፡ ቢያደርግ ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ።

፩ሺ.፩፻ ፺፭ ዐጥር ፡ ወደጎዳና ፡ ቢያዘነብል ፡ ባለአጥሩን ፡ እንዲያፈርሰው ፡ ቢለምኑት ፡ ቢያዳኙበትም ፡ ማፍረስ ፡ እየተቻለው ፡ በብዙ ፡ ቀን ፡ ባያፈርሰው ፡ በእርሱ ፡ መውደቅ ፡ በጠፋው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ዕዳ ፡ ይገባዋል ። ነፍስም ፡ ቢሆን ፡ ገንዘብም ፡ ቢሆን ፡ ማዘንበሉ ፡ ወደሌላው ፡ አጥር ፡ ቢሆን ፡ ያጥሩ ፡ ባለቤት ፡ እንዲያፈርሰው ፡ ይጠይቀው ። ያንድነቱ ፡ አጥር ፡ በሦስት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ቢሆን ፡ የጠፋውን ፡ ሦስተኛውን ፡ እጅ ፡ ሊከፍል ፡ ይገባዋል ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ እንዳያፈርሱት ፡ ሥልጣን ፡ ሲኖረው ፡ ባይከለከል ፡ ነው ።

፩ሺ.፩፻ ፺፮ ክፍል ። በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ የተነገረውን ፡ የሚከተል ፡ ነው ። ውሀ ፡ ከእርሷ ፡ ስለተከለከለ ፡ ወይም ፡ ውሀ ፡ በእርሷ ፡ ላይ ፡ ስለተበረታታባት ፡ የማትጠቅም ፡ ምድርም ፡ ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ከእርሱ ፡ ይልቅ ፡ በቀረበች ፡ አገር ፡ ካሉ ፡

ሀገር ፡ ዘትርብት ፡ እምኔሁ ፡ ወዘኢየእምሩ ሎቱ ፡ መላኪ ፡ ዘይመልኮ ፡ ይደልዎ ፡ ለባእሲ ከመ ፡ ይትገበር ፡ ቦቱ ፡ ወይምልኮ ። ወዘሰ ቦቱ ፡ አስረ ፡ ምርዓት ፡ ሕንጸ ፡ ይሕንጽ ፡ ወይሠኒ ፡ ጠፈረ ፡ ወዘሰ ፡ አልቦቱ ፡ አስረ ግብር ያሠኒ ፡ ሐጹረ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወይግበር ፡ ሎቱ ፡ አንቀጸ ። ወለገራህትሰ ፡ ያውፅእ ፡ ወያስተማኒ መሬቶ ፡ ወያውኅዝ ፡ ማየ ፡ ኀቤሃ ፡ ወምዕቃላትኒ ፡ ወአንቅዕታት ፡ ይከርዩ ፡ ኪያሆን ፡ ወለመዛግብትኒ ፡ ምዉራት ፡ ከመ ፡ ያውፅእን ።

፩ሺ.፩፻ ፺፯ ክፍል ፡ ወዘኢይትከፈል ፡ እምአብያተ ፡ ዘእሁ ፡ ወይበዋል ፡ በተከፍሎቱ ፡ በቀኖናት ፡ እንተ ፡ ግብርዋ ፡ በእንቲአሃ ፡ ዘከመ ፡ ቤተ ብለኔ ፡ ወአቶን ፡ ወማሕረፅ ፡ ወዓዘቅት ፡ ለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ፩ዱ ፡ እምተሳታፍያን ፡ ውስቴቱ ፡ ከመ ፡ ይሚጥ ፡ ክፍሎ ፡ ዘእሁ ፡ በእሙር ፡ አው ፡ ያስተበቍዕ ፡ ይደልዎ ፡ ለተሳታፊ ፡ በተማይጦተ ፡ ዘእሁ ፡ አው ፡ በተዓስቦቱ ፡ በዘይደልዎ ። ወውላኢሰ ፡ እንተ ፡ ተሰነአው ፡ ላዕሌሃ ፡ በተማይጦ ፡ አው ፡ በተዓስቦ ፡ ምስለ ፡ ካልእ ።

፩ሺ.፩፻ ፺፰ ወለእመ ፡ አእመረ ፡ ውኑዮ ፡ ይደልዎ ፡ ለጎሩ ፡ ዘይትላጸቅ ፡ ከመ ፡ ይንሣእ ፡ ወዘተማየጠሃ ፡ ከመ ፡ ያቅም ፡ ለጽኑሳን ፡ ሎቱ ፡ ይደሉ ፡ ወእለሰ ፡ ኢዘከርናሆሙ ፡ ይትበረዩ ። ወዘይደልዎ ፡ እምሉቱፋን ፡ በአምጣነ ፡ ክፍሎሙ ፡ ወእምዝ ፡ ለእግዋር ፡ እለ ፡ ልጹቃን ፡ በአምጣነ ፡ መፍቅዶሙ ፡ ዘይፈቅዱ ።

፩ሺ.፩፻ ፺፱ ወለእመ ፡ ተሰነአወ ፡ መላኪ ፡ ምስለ ፡ ካልእ እምተዳማዊ ፡ ወእመ ፡ ኮነ ፡ ተዳማዊ ፡ ዘአስምዐ በተማይጦቱ ፡ ላዕለ ፡ ፩ዱ ፡ እምተሰነአውያን ፡ በፈቃዶሙ ፡ በእንተ ፡ ተሰናእዎተ ፡ ሚጥ ፡ ወውሳኔያት ፡ እው ፡ አቀመ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ኢያሁብ ፡ እምቅድመ ፡ ተሰናእዎ ፡ ለካልኡ ፡ በጠለት ፡ ተሰናእዎቱ ፡ ዘምስለ ፡ ካልእ ፡ ወይለዎ ፡ ሎቱ ። ወለእመ ፡ ኢተጠየቀ ፡ ስምዕ ፡ ቃልኒ ፡ ቃለ ፡ ተዳማዊ ፡ ዘተማየጠ ፡ ምስለ ፡ መሐላሁ ።

፩ሺ.፪፻ ወለእመ ፡ ተድኅረ ፡ ተሰናእዎቱ ፡ ለተዳማዊ ፡ እምድኅረ ፡ እእምሮቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ምክንያት ፡ ከሙት ፡ ተበርዐ ፡ ቅድምናሁ ፡ ወከማሁ ፡ ተኀ



ሰዎች ፡ ስለመሠራቱ ፡ ቃል ፡ የማይስማማበትን ፡ ገንዘብ ፡ የሚያደርገው ፡ ባለቤቱን ፡ የማይአውቁለት ፡ መሬትን ፡ ለሰው ፡ ሊያርሰው ፡ ገንዘብ ፡ ሊያደርገው ፡ ይገባዋል ። የሕንፃ ፡ ሥርዓት ፡ ፍሊጋ ፡ (ባድማ) ፡ ያለበትን ፡ ግን ፡ ይሥራው ። ጠፈሩንም ፡ ያሳምር ። የሥራ ፡ ፍሊጋ ፡ (የጥንት ፡ ባድማ) ፡ የሌለውን ፡ ግን ፡ እጥሩን ፡ ያሳምር ። በርም ፡ ያውጣለት ። እርሻዋን ፡ ግን ፡ ያውጣት ። ( ይጥጋት ) ። መሬቷንም ፡ ያሳምር ። (ያለስልስ) ፡ ውሀ ፡ ያግባለት ። ረግረጎችና ፡ ምንጮች ፡ ቢሆኑ ፡ እነርሱን ፡ ይቆፍሩ ። የተሠወሩ ፡ ድልቦችንም ፡ እንዲያወጧቸው ፡ ይሁን ።

፩ሺ.፩፻ ፺፯ ክፍል ። ከቤቶቹ ፡ የማይከፈለውን ፡ ይናገራል ። ስለመከፈሉ ፡ በእርሷ ፡ ያደረጉት ፡ ጥቅም ፡ ይቀራል ። ይኸውም ፡ እንደ ፡ ውሽባ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ማድቤት ፡ እንደ ፡ ወፍጮ ፡ እንደ ፡ ውሀ ፡ ጉድጓድ ፡ ያለ ፡ ነው ። ከሸሪኮቹ ፡ አንዱ ፡ የታወቀ ፡ ድርሻውን ፡ ሊሸጥ ፡ ወይም ፡ ሊያከራየው ፡ ቢወድ ፡ መግዛቱ ፡ ወይም ፡ በሚገባ ፡ መከራየቱ ፡ ለሸሪኩ ፡ ይገባዋል ። ውሳኔስ ፡ በመግዛት ፡ ወይም ፡ በመከራየት ፡ ከሌላ ፡ ጋር ፡ በእርሷ ፡ ላይ ፡ የሚስማሙት ፡ ነው ።

፩ሺ.፩፻ ፺፰ አውቆ ፡ ቢተው ፡ በቅርብ ፡ ላለ ፡ ጎረቤቱ ፡ ሊወስድ ፡ ይገባዋል ። የገዛውም ፡ ሰው ፡ ለችግረኞች ፡ ሊሰጥ ፡ ይገባዋል ። ያልጠቀስናቸው ፡ ግን ፡ ይተካከሉ ። የሚገባውም ፡ ከሸሪኮች ፡ በየድርሻቸው ፡ ልክ ፡ ነው ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በቅርብ ፡ ላሉ ፡ ጎረቤቶች ፡ በሚሹት ፡ መፍቅዳቸው ፡ ልክ ፡ ነው ።

፩ሺ.፩፻ ፺፱ ባለገንዘብ ፡ የፊተኛውን ፡ ትቶ ፡ ከሌላ ፡ ጋራ ፡ ቢስማማ ፡ የመጀመሪያው ፡ ስለዋጋውና ፡ ስለ ፡ ውሉ ፡ በፈቃዳቸው ፡ ከተስማሙት ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ መግዛቱን ፡ ቢያሰማ ፡ ወይም ፡ ከሌላው ፡ ጋር ፡ ከመስማማቱ ፡ በፊት ፡ እርሱ ፡ እንደማይሰጥ ፡ ቢወስን ፡ ከሌላው ፡ ጋር ፡ መስማማቱ ፡ ቀረች ። ለእርሱም ፡ ተገባው ። ምስክሩ ፡ ባያረጋግጥ ፡ ቃሉ ፡ ከመሐላው ፡ ጋራ ፡ የገዛው ፡ የመጀመሪያው ፡ ሰው ፡ ቃል ፡ ነው ።

፩ሺ.፪፻ ካወቀ ፡ በኋላ ፡ ያለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ የመጀመሪያው ፡ ሰው ፡ ስምምነት ፡ ወደኋላ ፡ ቢል ፡ ቀዳሚነቱ ፡ ቀረ ። ከስም ፡ ያለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡

ንዋሂ ፡ ለእመ ፡ ተደኀረ ፡ ዘእንበለ ፡ ምክንያት ፡ ከሠተ ፡ ወለእመ ፡ ሞተ ፡ ቀዳማዊ ፡ በጠለ ፡ ቅድምናሁ ፡ ወ፩ዱ ፡ እምተሰነእውያን ፡ ለእመ ፡ ሞተ ፡ እኩ ፡ ዘትበጥል ።

ወደኋላ ፡ ቢል ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። መጀመሪያው ፡ ሰው ፡ ቢሞትም ፡ ቀዳሚነቱ ፡ ይቀራል ። ከተስማሙት ፡ አንዱ ፡ ቢሞት ፡ የምትቀር ፡ አይደለችም ።

## አንቀጽ ፡ ፴ወ፫ቱ ።

### በእንተ ፡ ልቃሕ ።

፩ሺ፪፻፩ ተሰናእዎሰ ፡ ዘልቃሕ ፡ ይደሉ ፡ ማእከለ ፡ ብዉሓን ፡ በእስተዋፅኦ ፡ ንዘክ ፡ ንዋይ ፡ ወኢትክውን ፡ እማነ ፡ ዘእንበለ ፡ በላዕለ ፡ ንዋይ ፡ እሙር ፡ በመድሎት ፡ ቅዉም ፡ ወበምግባኔ ፡ እምረባኅ ፡ እሙር ፡ እመሂ ፡ በዲናራት ፡ እው ፡ በካልእ ፡ እምዝንቱ ።

፩ሺ፪፻፪ ወኍሉቈ ፡ ውእቱ ፡ ሠረፀ ፡ ረባኅ ፡ ለ፩ዱ ፡ በመንፈቀ ፡ ያታ ፡ ወረባኅ ፡ መንፈቀ ፡ ያታ ፡ ለካልእ ፡ ፈረሆሙ ፡ እምተጋእዞ ።

፩ሺ፪፻፫ ወኢይደሉ ፡ ሥርዓተ ፡ ተሰናእዎ ፡ በሰድማኒ ፡ ዘኢይሠይጥ ፡ ግባሬ ፡ እምድኅሬሁ ፡ ወይከውን ፡ ሥርዓተ ፡ ተሰናእዎ ፡ በሰድማኒ ፡ ዘይሠይጡ ፡ እምድኅሬሁ ።

፩ሺ፪፻፬ ወይደልዎ ፡ ለተገባሪ ፡ ከመ ፡ ያስተጋብእ ፡ ወያስተዋፅእ ፡ ከመ ፡ መጋቢ ፡ ወኢይሣየጥ ፡ በዘይፈደፍድ ፡ እምሢጠ ፡ ምሳሌ ፡ ዘልማደ ፡ ሠይጥ ፡ ወኢይሢጥ ፡ በዘየሐጽጽ ፡ እምኔሃ ፡ በከመ ፡ ልማደ ፡ ንግድ ፡ ወኢ ፡ በሢጠ ፡ ስድማኒ ፡ ዘእንበለ ፡ ትሕቢት ፡ ወእኀዝ ፡ እንተ ፡ ትትረከብ ፡ ፅብጠቱ ፡ እምሳለ ፡ ውእቱ ፡ ወኢ ፡ ዘእንበለ ፡ ሢጥ ፡ ከሠተ ። ወኢይንሣእ ፡ ቦቱ ፡ ለነፍሱ ፡ በሢጥ ፡ ወበተሣይጦ ፡ ወኢይትለቃሕ ፡ እምኔሁ ፡ ወኢይሣየጥ ፡ ቦቱ ፡ በዘይፈደፍድ ፡ እምጥንተ ፡ ንዋየ ፡ ልቃሑ ፡ ወዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ ይደሉ ፡ በትእዛዘ ፡ እግዚአ ፡ ንዋይ ።

፩ሺ፪፻፭ ወዘሂ ፡ እስተዋፅኡ ፡ ኪያሁ ፡ በውስተ ፡ ንግድ ፡ በከመ ፡ ተሰነእዉ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ወእመሰ ፡ ኢተቀደመ ፡ ከዊነ ፡ ሁሳኔ ፡ ይኩን ፡ በእምግባኔ ፡ ተከፍሎቱ ፡ ለረባኅ ፡ ወለእመ ፡ አልቦቱ ፡ ረባኅ ፡ ይኩን ፡ እምንዋይ ።

፩ሺ፪፻፮ ወመስተገብርስ ፡ ምእመን ፡ እግዚእ ፡ ንዋይ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ መጋቢ ፡ ወቃልኒ ፡ ዚእሁ ፡

## አንቀጽ ፡ ፴፫ ።

### ስለ ፡ ብድር ፡ ይናገራል ።

፩ሺ፪፻፩ የብድር ፡ ስምምነት ፡ ግን ፡ ያንን ፡ ገንዘብ ፡ በማወጣጣት ፡ መብት ፡ ባላቸው ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ይገባል ። በታወቀ ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ በቀዋሚ ፡ ሚዛን ፡ ከታወቀ ፡ ትርፉም ፡ በልክ ፡ ካልሆነ ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ በሌላ ፡ ቢሆን ፡ እውነተኛ ፡ አይሆንም ።

፩ሺ፪፻፪ ከክርክር ፡ የተነሣ ፡ ፈርተው ፡ በዓይነቱ ፡ እኩሌታ ፡ ለአንዱ ፡ ትርፍ ፡ መሥራት ፡ ለሌላውም ፡ የዓይነቱን ፡ እኩሌታ ፡ ትርፍ ፡ መሥራት ፡ የተጠላ ፡ ነው ።

፩ሺ፪፻፫ ከእርሷ ፡ በኋላም ፡ ነጋዴ ፡ በማይሸጥባት ፡ ቀን ፡ የስምምነት ፡ ደንብ ፡ ማድረግ ፡ አይገባም ። ከእርሱ ፡ በኋላ ፡ በሚሸጡበት ፡ ቀን ፡ ግን ፡ የስምምነት ፡ ደንብ ፡ ማድረግ ፡ ይሆናል ።

፩ሺ፪፻፬ ለሠራተኛው ፡ (ለነጋዴ) ፡ ሹም ፡ እንደመሆኑ ፡ ሊያወጣጣ ፡ ሊሰበስብም ፡ ይገባዋል ። በመሸጥ ፡ ልማድ ፡ ከምሳሌ ፡ ዋጋ ፡ በሚበልጥ ፡ አይግዛ ። እንደ ፡ ንግድ ፡ ልማድ ፡ ከእርሷ ፡ በሚያንስ ፡ በዚህም ፡ አምሳል ፡ በዋስትናና ፡ ይዞታው ፡ በሚገኝ ፡ መያዣ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ወይም ፡ በታወቀ ፡ ዋጋ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በቀጠሮ ፡ (በዱቤ) ፡ ዋጋ ፡ አይሽጥ ። በመሸጥና ፡ በመግዛት ፡ ለራሱ ፡ አይጠቀምበት ። ከእርሱም ፡ አይበደር ። ከብድሩ ፡ ገንዘብ ፡ ተቀማጭ ፡ በሚበልጥ ፡ አይግዛበት ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ በባለገንዘቡ ፡ ትእዛዝ ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ።

፩ሺ፪፻፭ በንግድ ፡ ጊዜ ፡ ያወጣጡት ፡ ገንዘብም ፡ እርስ ፡ በእርሳቸው ፡ እንደተስማሙ ፡ ይሁን ። የውል ፡ ሁኔታ ፡ ባይቀድም ፡ ግን ፡ በትርፍ ፡ አከፋፈል ፡ ልክ ፡ ይሁን ። ትርፍ ፡ ባይኖርም ፡ ከገንዘቡ ፡ (ከዓይነቱ) ፡ ይሁን ።

፩ሺ፪፻፮ የታመነ ፡ ሠራተኛስ ፡ (ነጋዴስ) ፡ እስተዳዳሪ ፡ እንደመሆኑ ፡ የገንዘብ ፡ ጌታ ፡ ነው ። ከመሸ

ውእቱ ፡ በዘፈቀደ ፡ እምነ ፡ ሣጥ ፡ ወተሣየጠ ፡ ወእምነ ፡ ረባኅ ፡ ወእኅጕሎ ፡ ወምጣኔ ፡ ረባ ኅሰ ፡ ወሥርወ ፡ ንዋይ ፡ ለእመ ፡ ኢቆመ ፡ ስምዐ ፡ ጥዩቀ ፡ ዘያበጥል ፡ ቃሎ ። ወቀዳሚኒ ፡ በእጽሕፎ ፡ ስምዕ ፡ በሥርወ ፡ ንዋይ ፡ ወክ ፈለ ፡ ረባሕ ፡ ወሥርዓተ ፡ ውሳኔ ።

፩ሺ.፪፻፯ ወለበዓለ ፡ ንዋይ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይሥዐር ፡ በጊዜ ፡ ፈቀደ ፡ ወከማሁ ፡ ተገባሪኒ ፡ ለእመ ፡ ተከዘሎ ፡ ለበዓለ ፡ ንዋይ ፡ ከመ ፡ ያስተዋፅእ ፡ በንዋዩ ፡ እው ፡ ከመ ፡ ይኅድግ ፡ ላዕሌሁ ፡ ተገ ባሬ ፡ ካልእ ። ወለእመ ፡ ሞተ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔ ሆሙ ፡ እው ፡ ኀጥአ ፡ ልበ ፡ ተሥዕረ ፡ ተሰና እዎ ።

፩ሺ.፪፻፰ ወይደሉ ፡ ተከፍሎተ ፡ ንዋይ ፡ ዘበበያታሁ ፡ ወለእመ ፡ ኀሠሠ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ሠይጠ ፡ እምቅድመ ፡ ይትካፈሉ ፡ ይሰወ ፡ ሠይጥ ። ወእ መኒ ፡ ኮነ ፡ እምንዋየ ፡ ሊቃሕ ፡ ዕዳ ፡ ይሰዎ ፡ ለተገባሪ ፡ ከመ ፡ ይፍዲ ፡ ወለእመ ፡ ሀሎ ፡ ላዕለ ፡ ለቃሒ ፡ ከዊነ ፡ ሊቃሕ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ፡ ይፍዲ ፡ እምቅድመ ፡ ኵሉ ።

ስለ ፡ መታመን ።

ዋና ፡ ከመግዛት ፡ ከትርፋና ፡ ኪሣራ ፡ በወደደ ፡ ገንዘብ ፡ የትርፉ ፡ ልክና ፡ የንገንዘቡ ፡ ዓይነትም ቃሉን ፡ የሚያፈርስ ፡ የማስረጃ ፡ ምስክር ፡ ካላ ስመሰከረ ፡ ነገሩ ፡ የእርሱ ፡ ነው ። መጀመሪ ያም ፡ በገንዘቡ ፡ ዓይነትና ፡ በትርፉ ፡ አከፋ ፈል ፡ በውሉም ፡ ደንብ ፡ ምስክር ፡ በማጻፍ ፡ ነው ።

፩ሺ.፪፻፯ ባለገንዘብም ፡ በወደደ ፡ ጊዜ ፡ ሊሽር ፡ ይገባ ዋል ። ሠራተኛም ፡ (ነጋዴ) ፡ ለባለገንዘብ ፡ በገ ንዘቡ ፡ ሊያወጣጣ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ሠራተኛ ፡ ሊሾም ፡ ቢቻለው ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። ከእነርሱ፡ አንዱ ፡ ቢሞት ፡ ወይም ፡ አእምሮውን ፡ ቢያጣ፡ ስምምነቱ ፡ ፈረሰ ።

፩ሺ.፪፻፰ የገንዘቡም ፡ አከፋፈል ፡ በያይነቱ ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ። ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ ከመካፈላቸው ፡ አስቀድሞ ፡ ሊሸጥ ፡ ቢፈልግ ፡ መሸጥ ፡ ተገ ባው ። ከብድሩም ፡ ገንዘብ ፡ ቢሆን ፡ ለሠራተ ኛው ፡ (ለነጋዴው) ፡ ዕዳ ፡ ተገባው ። ባበዳሪ ፡ ላይ ፡ የብድር ፡ ሁኔታ ፡ ቢኖርበት ፡ ከሁሉ ፡ አስ ቀድሞ ፡ ሊከፍል ፡ ይገባዋል ።

## አንቀጽ ፡ ፴ወ፱ቱ ፡

በእንተ ፡ ተአምኖ ።

፩ሺ.፪፻፱ ወውእቱ ፡ ፬ቱ ፡ አክፋል ። ክፍል ፡ ቀዳማዊ ፡ ለእመ ፡ ተአመነ ፡ እግዓዚ ፡ ብጹሐ ፡ እምዓመ ፡ በንጹሕ ፡ በአበሳሁ ፡ ይሰዎ ፡ ንስሐ ፡ በእንቲአሁ፡ እመኒ ፡ በንዋይ ፡ ይደልዎ ፡ ፈድዮቱ ።

፩ሺ.፪፻፲ ወለዘሰ ፡ ሀሎ ፡ ታሕተ ፡ ምግብ ፡ በእንተ ፡ ናእሱ ፡ እው ፡ በእንተ ፡ ዕበዱ ፡ ኢይከውን ፡ እማነ ፡ ተአምኖተ ፡ አበሳሆሙ ፡ ወኢ ፡ በነ ሢአ ፡ ንዋይ ፡ ወላዕለ ፡ ወቃሲ ፡ ይደሉ ፡ አቅ ሞተ ፡ ሰማዕት ፡ በምጣኔ ፡ አካል ፡ ወበልቡ ናሁ ። ወለዘሀሎ ፡ ታሕተ ፡ ምግብ ፡ በካልእ ፡ እምዝንቱ ፡ ይከውን ፡ እማነ ፡ ተአምኖቱ ፡ በዘይደልዎ ፡ ኵነኔ ፡ ተማግጾ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘታሕተ ፡ ምግብ ፡ ሀብይ ፡ ኢይከውን ፡ እማነ ፡ ተአምኖቱ ፡ በንዋይ ፡ በእንተ ፡ ዕበይ ፡ ዚአሁ ።

## አንቀጽ ፡ ፴፱ ።

ስለ ፡ መታመን ፡ ይናገራል ።

፩ሺ.፪፻፱ ይኸውም ፡ አራት ፡ ክፍል ፡ ነው ። መጀመሪያ ፡ ክፍል ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያደረሰ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ሰው ፡ በንጹሕ ፡ በደሉን ፡ ቢያምን ፡ ስለዚህ ፡ ንስሓ ፡ ተገባው ፡ በገንዘቡም ፡ ቢሆን ፡ መክ ፈል ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ.፪፻፲ ስለ ፡ ልጅነቱ ፡ ወይም ፡ እእምሮውን ፡ ስለማ ጣቱ ፡ በመተዳደር ፡ ሥር ፡ ያለ ፡ ግን ፡ በደሉን ፡ ወይም ፡ ገንዘብ ፡ መውሰዱን ፡ ማመኑ ፡ እው ነት ፡ አይሆንም ። ለተከራካሪውም ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ በማድረሱና ፡ በአእምሮው ፡ መያላ ደል ፡ ምስክር ፡ መጥራት ፡ ይገባዋል ። ከዚህ ፡ በሌላ ፡ ከአስተዳደር ፡ በታች ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ የቅ ጣት ፡ ፍርድ ፡ በሚገባው ፡ ገንዘብ ፡ መታመኑ ፡ እውነት ፡ ይሆናል ። ከአስተዳደር ፡ በታች ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ እእምሮውን ፡ ያጣ ፡ ቢሆን ፡ በገንዘቡ ፡ መታመኑ ፡ እእምሮውን ፡ ስለማ

፩ሺ.፪፻፲፩ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ በኀበ ፡ ዕዳ ፡ ዘኀጥአ ፡ ፈድየ ፡ ዘእሃ ፡ ይለያ ፡ ተአምኖ ፡ በንዋይ ፡ ወኢይደሉ ፡ ቀዊም ፡ ቦቱ ፡ በጊዜ ፡ አላ ፡ እምድኅረ ፡ ፈድየ ፡ ዕዳ ፡ ዘቀዳማዊ ፡

፩ሺ.፪፻፲፪ ወለግብርኒ ፡ ይከውን ፡ እማነ ፡ ተአምኖቱ ፡ በንዋይ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘኢያበውሕዎ ፡ ይደልዎ ፡ ዕዳ ፡ እምድኅረ ፡ ማዕዘኑ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ብእሲ ፡ ውስተ ፡ ተግባር ፡ እንተ ፡ አሰተብውሑ ፡ ሎቱ ፡ ውስቴታ ፡ እግዚኡ ፡ ይደልዎ ፡ ፈድየ ፡ ዕዳሁ ፡ ለእግዚኡ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ውስተ ፡ ካልእታ ፡ ይለዎ ፡ እምረባኁ ፡ ወለእመ ፡ ኢኮነ ፡ ሎቱ ፡ ረባኅ ፡ ይለዎ ፡ እምድኅረ ፡ ማዕዘኑ ።

፩ሺ.፪፻፲፫ ወዳግማዊኒ ፡ ዘይትአመኑ ፡ ሎቱ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ጠቢበ ፡ ትእዛዙ ፡ ከመ ፡ ኢይክላእ ፡ ወኢየሐስ ፡ ዘተአመነ ፡ ወለእመ ፡ ኢኮነ ፡ ለባዌ ፡ ትእዛዙ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ እምዘይትበቋዕ ፡ በዘተአመንዎ ፡ ቦቱ ፡ ሎቱ ። ወበኢይፈቅድ ፡ በእንተ ተወክፎ ፡ ዘተአመንዎ ፡ ሎቱ ፡ ያስተጋብእ ፡ ጋእዘ ፡ ዘከመ ፡ ውስተ ፡ ክርሥ ፡ ብእሲት ። ወዘተአመነ ፡ ለፅንስ ፡ ንዋይ ፡ እምርስት ፡ አው ትእዛዝ ፡ እንተ ፡ ተጽሕፈ ፡ ቆመ ፡ ሎቱ ፡ ለእመ ተወልደ ፡ ሕያወ ፡ ለንኡስኒ ፡ ወለዘብድ ፡ ዘተአመኑ ፡ ሎሙ ፡ በንዋይ ፡ ቆመ ፡ ሎሙ ። ወለግብርኒ ፡ ዘተአመነ ፡ ሎቱ ፡ ንዋይ ፡ ይከውን ፡ ለእግዚኡ ። ወለእመ ፡ ተአመነ ፡ ንዋይ ፡ ለምኔት ፡ ይደልው ፡ ለእለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስቴታ ።

፩ሺ.፪፻፲፬ ሣልስኒ ፡ ዘይትአመኑ ፡ ቦቱ ፡ መዘንቱኒ ፡ እኩ፡ እምተከህሎቱ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ክሡተ ፡ ወእምሉኩ ፡ ለተአማኒ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይከውን ፡ እማነ ፡ ተአምኖ ፡ በዐብድ ፡ ወበዘኢይትመለክ ፡ አላ ፡ ለእመ ፡ ኢኮነ ፡ መላኬ ፡ በጠለ ፡ ተአምኖቱ ፡ ቦቱ ። እስመ ፡ ውእቱ ፡ ሰበ ፡ ይቤ ፡ ዓበደየ ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ዘእቀንየ ፡ በውስተ ፡ እዴየ ፡ ይእቲ ፡ እምሥርዓተ ፡ ውሳኔ ፡ ለእገሌ ፡ ኢይኩን ፡ እስመ ፡ ኢኮነ ፡ ሎቱ ፡ ምልኩተ ፡ ኢይኩን ፡ ለግብር ፡ ዘከመ ፡ ምልክናሁ ፡ ሎቱ ፡ ምልክና ፡ ካልኡ ፡ አላ ፡ ይሰነእዉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ ወሥርዓቱ ። እስመ ፡ ውእቱ ፡ ለእመ ፡ ተአመነ ፡ በማዕዘነ ፡ ገብር ፡ ዘውስተ ፡ እደ ፡ ካልኡ ፡ ኢይከውን ፡ እማነ ።

፩ሺ.፪፻፲፭ ራብዕኒ ፡ ቃለ ፡ ተአምኖት ፡ ወፍካሬ ፡ ቃልስ ፡

ማቱ ፡ እውነት ፡ አይሆንም ።

፩ሺ.፪፻፲፩ ዕዳ ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ እርሱን ፡ ለመክፈል ፡ ያጣ ፡ ቢሆን ፡ በገንዘቡ ፡ ማመን ፡ ይገባዋል ። ያንጊዜ ፡ ሊያስገድዱት ፡ አይገባም ። የመጀመሪያውን ፡ ዕዳ ፡ ከከፈለ ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፩ሺ.፪፻፲፪ ባሪያ ፡ በገንዘብ ፡ መታመኑ ፡ ዕውነት ፡ ይሆናል ። ሥልጣን ፡ ያልሰጡት ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ከነፃነቱ ፡ በኋላ ፡ ዕዳ ፡ ይገባዋል ። ጌታው ፡ በፈቀደለት ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ የሠለጠነ ፡ ቢሆን ፡ ዕዳውን ፡ ሊከፍልለት ፡ ለጌታው ፡ ይገባዋል ። በሌላዋ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ከትርፉ ፡ መክፈል ፡ ተገባው ። ትርፍ ፡ ባይኖረው ፡ ከነፃነቱ ፡ በኋላ ፡ ሊከፍል ፡ ተገባው ።

፩ሺ.፪፻፲፫ ሁለተኛውም ፡ የሚታመኑለትን ፡ ይናገራል ። ዐዋቂ ፡ ቢሆን ፡ ትእዛዙ ፡ እንዳይከለክል ፡ ያመነውን ፡ እንዳይዋሽ ፡ ነው ። ዐዋቂ ፡ ባይሆንም ፡ ትእዛዙ ፡ እርሱን ፡ ባመኑበት ፡ ገንዘብ ፡ ከሚጠቀምበት ፡ ወገን ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ያመኑለትን ፡ ለመቀበል ፡ የማይሻ ፡ ቢሆ ፡ ክርክርን ፡ ያይሰበስባል ። ይኸውም ፡ በሴት ፡ ማኅፀን ፡ እንዳለ ፡ ያለ ፡ ነው ። ለጽንስ ፡ ከርስት ፡ የታመነ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ የተጻፈ ፡ ትእዛዝ ፡ ሕያው ፡ ሆኖ ፡ ቢወለድ ፡ ጸናለት ። ለትንሽና ፡ ላለአዋቂም ፡ በገንዘብ ፡ ያመኑላቸው ፡ ጸናላቸው ። ለባሪያም ፡ የታመነለት ፡ ገንዘብ ፡ ለጌታው ፡ ይሆናል ። ለገዳምም ፡ ገንዘብ ፡ ቢታመን ፡ በውስጧ ፡ ለሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ይገባል ።

፩ሺ.፪፻፲፬ ሦስተኛውም ፡ የሚታመኑበትን ፡ (ገንዘብ) ፡ ይናገራል ። ይህም ፡ ከታማኙ ፡ ከችሎቱ ፡ የተነጣ ፡ የተገለጸና ፡ የተገዛ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ እይደለም ። አእምሮውን ፡ በእብድ ፡ በማያዝዝ ፡ ዘንድ ፡ መታመን ፡ እውነት ፡ ይሆናልና ። ባለገንዘብ ፡ ባይሆን ፡ በእርሱ ፡ ማመኑ ፡ ፈረሰ ፡ እንጂ ። ከውሳኔ ፡ ሥራት ፡ የተነሣ ፡ በእጁ ፡ ውስጥ ፡ ያለች ፡ የማስተዳደሪያ ፡ በታዬ ፡ ናትና ፡ ለእገሌ ፡ ሽጬለታለሁ ፡ ቢል ፡ አይሆንም ። ገንዘቡ ፡ አይደለችምና ። የሌላውን ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ ገንዘቡ ፡ አድርጎ ፡ በማድ ፡ አይሆንም ። በእጁና ፡ በሥርዓቱ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ይስማማ ፡ እንጂ ። በሌላ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ባለ ፡ በባሪያ ፡ ነፃነት ፡ ቢታመን ፡ የታመነ ፡ አይሆንምና ።

፩ሺ.፪፻፲፭ አራተኛውም ፡ ስለ ፡ መተማመን ፡ ቃል ፡ ይና

ዘተአመነ ፡ ሳዕለ ፡ ነፍሱ ፡ ወይቤ ፡ በእንቲአ ፡ ላዕሌየ ፡ አው ፡ በኀቤየ ፡ አው ፡ ዕዳ ፡ በርእስየ ፡ አው ፡ እመ ፡ ይቤ ፡ ካልእ ፡ ሊተ ፡ በላዕሌሁ ፡ አው ፡ በኀቤሁ ፡ አው ፡ ዕዳ ፡ በርእሱ ። ወለእመ፡ ውእቱ ፡ ይቤ ፡ ሎቱ ፡ በላዕሌየ ፡ አው ፡ በኀቤየ ፡ አው ፡ ዕዳ ፡ በርእስየ ፡ አው ፡ መጽወትከ ፡ አው ፡ አነ ፡ ተአማኒ ፡ ቦቱ ፡ አው ፡ አንሰ ፡ ዘኢይክሕድ ፡ ቦቱ ፡ አው ፡ እወ ፡ አው ፡ ዘይመስሎ ፡ ለዝንቱ ፡ ከሙት ፡ በኀበ ፡ ሰብአ ፡ መዝንቱ ፡ ኮሉ ፡ ውእቱ ፡ ተአምኖ ። ወለእመ ፡ ይቤ፡ አነ፡ እአምን፡ኪያሁ፡ወኢይክሕዶ፡ውእቱኒ ፡ ተአምኖት ፡ በተአምኖ ፡ ዘይመጽእ ። ወለእመ ፡ ይቤ ፡ ንግእ ፡ አው ፡ ድሉ ፡ አው ፡ ፈጽም ፡ በዘይደሉ ፡ መዝንቱ ፡ ኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ እምፍኖተ ፡ ሰላት ፡ ወተአምኖቲኒ ፡ ኢይኅሬ ።



ገራል ። በራሱ ፡ ላይ ፡ የታመነው ፡ የቃል ፡ ትርጓሜ ፡ ግን ፡ እንደዚህ ፡ ነው ። የእገሌ ፡ ገንዘብ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ወይም ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ነው። ወይም ፡ ዕዳ ፡ በራሴ ፡ አለብኝ ፡ ቢል ፡ ወይም ፡ ሌላው ፡ ለኔ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ዕዳ ፡ በራሱ ፡ አለበት ፡ ቢል ፡ እርሱም ፡ የእርሱ ፡ ገንዘብ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ወይም ፡ ዕዳ ፡ በራሴ ፡ አለብኝ ፡ ቢል ፡ ወይም ፡ መጽወትኩት ፡ ወይም ፡ እኔ ፡ አምንበታለሁ ፡ ወይም ፡ የማልክድበት ፡ ነው ፡ ወይም፡ አዎን ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የሚመስለውን ፡ በሰው ፊት ፡ የተገለጸውን ፡ ቢል ፡ ይህም ፡ ሁሉ ፡ መታማመን ፡ ነው ። እኔ ፡ እርሱን ፡ አምነዋለሁ ፡ አልክደውም ፡ ቢል ፡ የሚመጣውን ፡ በመታማመን ፡ እምነት ፡ ይህ ፡ ነዋ ። ውሰድ ፡ ወይም ፡ መዝን ፡ ወይም ፡ በሚገባ ፡ ፈጽም ፡ ቢል ፡ ይህ ፡ ከዝብብት ፡ ወገን ፡ ሊሆን ፡ አይገባም ። መታመኑም ፡ አይረባም ።

፩ሺ፪፻፲፯ ወትርጓሜሁሰ ፡ እመ ፡ ተአመነ ፡ በዘኢይትዐወቅ ፡ ከዋኔሁ ፡ ምንትኑ ፡ አው ፡ በንዋይ ፡ ዘየጎሥሥዎ ፡ በከዋኔሁ ፡ ወሎቱ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይክሥቶ ፡ በዘየሐጽጽ ፡ ለዘይትከሀል ፡ እምዘይደሉ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘነገረ ፡ ኪያሁ ፡ በስበይ ፡ ወአብዝኆ ፡ ይመረ ፡ ውሳኔ ፡ በከዋኔሁ ፡ ወውኅደቱሰ ፡ ውብዝኅት ፡ መበኑ ፡ ፲ቱ ፡ ድርህማት ። ወለእመ ፡ ይቤ ፡ ድርህማት ፡ ወውኅደቱ ፡ ዚአሆን ፡ ፲ቱ ፡ ወለእመ ፡ ይቤ ፡ ከመዝ፡ ወከመዝ ፡ ድርህማት ፡ ይከውን ፡ ውኅደቱን ፡ ፲ወ፩ዱ ። ወለእመ ፡ ይቤ ፡ ከመዝ ፡ ወከመዝ ፡ ሐጸጸ ፡ ድርህማት ፡ ፳ወ፩ዱ ። ወለእመ ፡ ይቤ ፡ ሎቱ ፡ በላዕሌየ ፡ አው ፡ በኀቤየ ፡ አው ፡ ዕዳ ፡ በርእስየ ፡ ናሁ ፡ ተአመነ ፡ በዕዳ ፡ ተሰትሖ ። ወእመ ፡ ይቤ ፡ ሎቱ ፡ ኀቤየ ፡ አው ፡ ምስሌየ ፡ አው ፡ በቤትየ ፡ አው ፡ በማዕጉየ ፡ አው ፡ ታሕተ እዴየ ፡ መዝንቱ ፡ ተአምኖ ፡ በአንብሮ ፡ ማኅበንት ፡ አው ፡ በውሕስት ፡ አው ፡ በአማዝ ።

፩ሺ፪፻፲፯ ትርጓሜው ፡ ግን ፡ ሁኔታው ፡ ምንም ፡ በማይታወቅ ፡ ወይም ፡ በሁኔታው ፡ በሚፈላለጉት ፡ ገንዘብ ፡ ቢታመን ፡ የሚገባ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ለሚቻለው ፡ በሚያንስ ፡ ሊገልጠው ፡ ለእርሱ ፡ ይገባዋል ። ከፍ ፡ በማድረግና ፡ በማብዛት ፡ እርሱን ፡ የተናገረ ፡ ቢሆን ፡ በሁኔታው ፡ ጭማሪውን ፡ አበዛ ። ማነስና ፡ መብዛትስ ፡ በአሥር ፡ ድርህሞች ፡ ልክ ፡ ነው ። ድርህማት ፡ ጉድለታቸውም ፡ ሦስት ፡ ነው ፡ ቢል ፡ ድርህማትም ፡ እንዲህና ፡ እንዲህ ፡ ናቸው ፡ ቢል ፡ ጉድለታቸው ፡ አሥራ ፡ አንድ ፡ ይሆናል ። እንዲህና ፡ እንዲህ ፡ ቢልም ፡ የድርህማት ፡ ቅናሽ ፡ ኻያ ፡ አንድ ፡ ነው ። ለእርሱ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ አለው ፡ ወይም ፡ በራሴ ፡ ዕዳ ፡ አለብኝ ፡ ቢል ፡ በብድር ፡ ዕዳ ፡ እነሆ ፡ ታመነ ። ለእርሱ ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ወይም ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ወይም ፡ በቤቴ ፡ ወይም ፡ በግዋኔ ፡ ወይም ፡ በእጄ ፡ ውስጥ ፡ አለብኝ ፡ ቢል ፡ ይህ ፡ መተማመን ፡ አደራ ፡ በማኖር ፡ ወይም ፡ በማዋስ ፡ ወይም ፡ በመያዣ ፡ ነው ።

፩ሺ፪፻፲፰ ወኮሉ ፡ ዘበጽሑ ፡ ቃለ ፡ ተአምኖቱ ፡ በቃል፡ ይበሪሉ ፡ ኮለንታሁ ፡ ዘዚአሁ ፡ አው ፡ መንፈቀ ፡ ወዘይበጽሕ ፡ ኮለንታሁ ፡ አው ፡ መንፈቀ ፡ ዚአሁ ፡ ከመ ፡ ዘይብል ፡ ዛቲ ፡ ዓፀድ ፡ ዚአከ ፡ ወባሕቱ ፡ ሀተብከዋ ፡ አው ፡ ለውሉ

፩ሺ፪፻፲፰ የቀረበው ፡ በቃል ፡ የመተማመን ፡ (ነገር) ፡ ሁሉ ፡ የእርሱ ፡ ሁለንተናው ፡ ወይም ፡ እኩሌታው ፡ ይቀራል ፡ መላው ፡ ወይም ፡ የእርሱ ፡ እኩሌታ ፡ የሚቀረውስ ፡ ይህች ፡ ቦታ ፡ ያንተ ፡ ወይም ፡ የልጆችህ ፡ ናት ። ነገር ፡ ግን ፡ ጠበት

ድኅ ፡ አው ፡ አልበልኒ ፡ ጠፈረ ፡ ዚአሃ ፡ አው ፡ አንተ ፡ ኀደርከ ፡ ዘእንበለ ፡ ምልክናሃ ፡ አው ፡ በሥርዓተ ፡ ውሳኔ ፡ ከመ ፡ ትድሉ ፡ ግሒጠ ፡ ዚአሃ ።

፩ሺ፪፻፲፰ ወዘሂ ፡ ተአመነ ፡ በክዋኔ ፡ ዘመድ ፡ ይደልዎ ፡ ለእመ ፡ ኢየሐሰዎ ፡ ሕሊናሁ ፡ አው ፡ ሥርዓተ ፡ ጥያቄ ፡ አው ፡ ከመ ፡ ዘይብል ፡ ከመ ፡ ዝንቱ ፡ ወልድየ ፡ ወይከውኑ ፡ ዕሩያነ ፡ በዕድሜ ፡ ሕይወት ፡ አው ፡ ይከውን ፡ ሎቱ ፡ ለዘተአመነ ፡ ካልእ ፡ ዘመድ ፡ ዕውቅ ፡ አው ፡ ያመጽኡ ፡ ሎቱ ፡ ማእከሌሁ ፡ ወራስያኒሁ ፡ ለዘተአመነ ፡ ስምዐ ፡ ጥያቄ ፡ ለአብጥሎቱ ፡ ተአምኖቱ ።

ከጠፋ ፡ በኋላ ፡ ስለሚገኝ ።

ኋት ፡ ወይም ፡ ጠፈሯን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረግ ኳት ። ወይም ፡ ያለ ፡ ገንዘብነቷ ፡ ወይም ፡ በውሳኔ ፡ ደንብ ፡ ዋጋዋን ፡ ልትገምት ፡ አንተ ፡ አደርህባት ፡ እንደሚል ፡ ነው ።

፩ሺ፪፻፲፰ ዘመድ ፡ በመሆን ፡ የታመነም ፡ ሕሊና ፡ ወይም ፡ የጥያቄ ፡ (የማረጋገጫ) ፡ ሥርዓት ፡ ካላጠራጠረው ፡ ይገባዋል ። ወይም ፡ ይህ ፡ ልጄ ፡ ነው ፡ እንደሚል ፡ ነው ። በሕይወት ፡ ዘመን ፡ የተካከሉ ፡ ይሆናሉ ። ወይም ፡ ለታመነ ፡ ሰው ፡ የታወቀ ፡ ሌላ ፡ ዘመድ ፡ ይሆን ለታል ። ወይም ፡ በመካከሉ ፡ የታመነው ፡ ሰው ፡ ወራሾቹ ፡ መታመኑን ፡ ለማስቀረት ፡ የማስረጃ ፡ ምስክር ፡ ያመጡለታል ።

## አንቀጽ ፡ ፵ ፡

በእንተ ፡ ዘይትረከብ ፡ እምዘ ፡ ተኅጥአ ፡ ወበእንተ ፡ ዘጕየ ፡ በመካናተ ፡ ተሳትፎ ፡ ዘከመ ፡ ገዳም ፡ ወፍኖት ፡ ወምሥያጥ ፡ ወቤተ ፡ ብለኔ ፡ ወቤተ ፡ ንግድ ፡ ወቤተ ፡ ክርስቲያን ።

፩ሺ፪፻፲፱ ወዝንቱ ፡ ሥሩዕ ፡ ውእቱ ፡ ውስተ ፡ ኦሪት ፡ ሕጉ ፡ በቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘይቤ ፡ እግብእ ፡ ዘተገድፈ ፡ ለእኁከ ፡ ወእመኒ ፡ ኢኮነ ፡ ቅሩበ ፡ ወኢተአምሮ ፡ አብእ ፡ ኀበ ፡ ማኅደርከ ወየሀሉ ፡ ኀቤከ ፡ እስከ ፡ የኀሥሥ ፡ እኁከ ፡ ወታግብእ ፡ ሎቱ ፡ እንስሳሁ ፡ ወልብሰ ፡ ወኵሎ ፡ ግዱፈ ፡ እኁ ፡ ሠናይ ፡ ለከ ፡ ትትኀየይ ፡ ኪያሆሙ ፡ ወዝንቱ ፡ ኀበ ፡ ፪ቱ ፡ ክፍል ።

## አንቀጽ ፡ ፵ ።

ከጠፋ ፡ በኋላ ፡ ስለሚገኝ ፡ በአንድነት ፡ (በጋርዮሽ) ፡ በታዎች ፡ ስለኮበለለም ፡ ይናገራል ። ይኸውም ፡ እንደ ፡ ዱር ፡ እንደ ፡ ጎዳና ፡ እንደ ፡ ገበያ ፡ እንደ ፡ ውሽባ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ እንግዳ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ያለ ፡ ነው ።

፩ሺ፪፻፲፱ ይኸውም ፡ በሕጉ ፡ ኦሪት ፡ ለወንድምህ ፡ የጠፋውን ፡ ገንዘብ ፡ መልስለት ፡ ተብሎ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ የተጻፈ ፡ ነው ። ምንም ፡ ቅርብ ፡ ባይሆን ፡ ባታውቀውም ፡ ወደቤትህ ፡ አስገባው ። ወንድምህ ፡ እስኪሻው ፡ ድረስ ፡ በአንተ ፡ ዘንድ ፡ ይኑር ። ከብትም ፡ ቢሆን ፡ ልብስም ፡ ቢሆን ፡ የጠፋውን ፡ ሁሉ ፡ መልስለት ። እነርሱን ፡ ቸል ፡ ልትል ፡ ለአንተ ፡ ደግ ፡ አይደለም ። (ዘፀ ፡ ፳፫ ፡ ፬) ። ይህም ፡ ፪ ፡ ክፍል ፡ ነው ።

፩ሺ፪፻፳ ቀዳማዊ ፡ በእንተ ፡ ንዋይ ፡ ዘይፈልስ ፡ ውስተ ፡ መካናት ። ወዘረከበ ፡ ምንተኒ ፡ ዘኢይትዐወቅ ፡ ሎቱ ፡ መላኪሁ ፡ በውእቱ ፡ ጊዜ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ንኡስ ፡ ዘኢይነዝኖ ፡ ተኅጥኦቱ ፡ ለዘጠፍአ ፡ እምኔሁ ፡ ይኅሥሥ ፡ ወየአምሮ ፡ ፩ደ ፡ ሱባኤ ፡ በመካን ፡ ዘረከቦ ፡ በውስቴቱ ፡ ወበካልእ ። ወለእመ ፡ በጽሐ ፡ ዘይዜክሮ ፡ ለበዓለ ፡ ዚአሁ ፡ ወእምነገራቲሁ ፡ ወእምከመ ፡ ሞዐ ፡ ትሕዝብተ ፡ ሕሊናሁ ፡ ከመ ፡ ለሊሁ ፡ ውእቱ ፡ ያግብእ ፡ ሎቱ ፡ ወእመ ፡ አኮሰ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይትመጠብ ፡ ቦቱ ።

፩ሺ፪፻፳ መጀመሪያው ፡ ወደቦታዎች ፡ ስለሚዛወር ፡ ገንዘብ ፡ ይናገራል ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ባለቤቱ ፡ ያልታወቀለትን ፡ ማናቸውንም ፡ ያገኘ ፡ ሰው ፡ ከእርሱ ፡ ለጠፋበት ፡ ሰው ፡ መጥፋቱ ፡ የማያሳዝነው ፡ ትንሽ ፡ ቢሆን ፡ ወሰዶ ፡ አንድ ፡ ሳምንት ፡ በውስጡ ፡ ባገኘበት ፡ ቦታና ፡ በሌላውም ፡ ያመልከት ። ከነገሩ ፡ የተነሣ ፡ ባለቤቱን ፡ የሚያስታውስ ፡ ቢደርስ ፡ የእርሱም ፡ እንደሆነ ፡ የሕሊናው ፡ ጥርጥር ፡ ካቸነፈ ፡ ይመልስለት ። ያለዚያ ፡ እርሱ ፡ ሊተዳደርበት ፡ ይገባዋል ።

አንቀጽ ፡ ፵ ።

፩ሺ፪፻፳፩ ወለእመ ፡ ኢኮነ ፡ መጠኑ ፡ ንኡስ ፡ ወብዙ ኀኑ ፡ የኀንዝኑ ፡ በእንተ ፡ ተኀጥኦቱ ፡ ለዘተኀጕለ ፡ መፍትው ፡ ከመ ፡ ይንሥኦ ፡ በሕልዮተ ፡ ተዓቅቦቱ ፡ ለመላኪሁ ፡ ወያስተሐይጽ ፡ ከዋኔሁ ፡ ወያእምር ፡ አርእያሁ ፡ ወምጣኔሁ ፡ ውኀበ ፡ ያኀብር ። ወይደልዎ ፡ ከመ ፡ ያስምዕ ፡ ላዕለ ፡ ነፍሱ ፡ ወይገብር ፡ ለስማዕታት ፡ መንፈቀ ፡ አርእያሁ ፡ ዘይትፈለጥ ፡ ቦቱ ፡ ከመ ፡ ኢየሀብ ፡ ምክንያተ ፡ ለሰይጣን ፡ ለአስሕቶቱ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ።

፩ሺ፪፻፳፪ ወእምዝ ፡ ይንግር ፡ ዜናሁ ፡ በበኵሉ ፡ ሰባኤ ፡ እስከ ፡ ሰቡዕ ፡ ሰባዔ ፡ በመካን ፡ ዘረከቦ ፡ ቦቱ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ሕኑጸ ፡ ወእምዝ ፡ ለእለ ፡ በዓ ውዱ ፡ ወእምዝ ፡ በመካን ፡ ጉባኤያት ፡ ዘከመ ፡ መራኅብት ፡ ወምሥያጣት ። ወይገብር ፡ መን ፈቀ ፡ አርእያሁ ፡ ዘያዓውቅ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ለመኑኑ ፡ ዘጠፍኦ ፡ ድርህማቲሁ ፡ ወባሕቱ ፡ ኢይገብር ፡ አምሳሊሃ ፡ ወኢመደሎታ ፡ ወኢ ግጸ ፡ ቍናማታ ፡ አው ፡ መኑ ፡ ዘጠፍአ ፡ ሎቱ ፡ ንዋየ ፡ ንህበት ፡ አው ፡ ልብስ ፡ ወኢይገብር ፡ ኅብረቲሁ ፡ ወኢ ፡ አርእያሁ ፡ ወኢከዋኔሁ ።

፩ሺ፪፻፳፫ ወእመቦ ፡ ዘመጽአ ፡ ወነገረ ፡ ከመ ፡ ዘጠ ፍአ ፡ ቢእሁ ፡ ውእቱ ፡ ወዘከረ ፡ መብዝኅተ ፡ ትእምርታቲሁ ፡ እስከ ፡ ይመውዕ ፡ ላዕለ ፡ ትሕ ዝብት ፡ ከመ ፡ ሊሊሁ ፡ ውእቱ ፡ ያግብኦ ፡ ሎቱ፡ እምድኅረ ፡ ኮኑ ፡ ሰማዕተ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወበሀል ዎቶሙ ፡ ለእለ ፡ የአምርዎ ፡ ወይደሉ ፡ ከመ ፡ ያምጽእ ፡ አማእዜ ፡ ምእመነ ፡ ዘሰምዐ ፡ ይከ ውኖ ፡ ሎቱ ። ወለእመ ፡ ኢበጽሐ ፡ በስድማ ፡ መላኪሁ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይሥራዕ ፡ ውስ ቴቱ ።

፩ሺ፪፻፳፬ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ለዕዱ ፡ ገብረ ፡ እእምሮቱ ፡ ወቅንየቱ ፡ ወምልክናሁ ፡ ይከውን ፡ ለእግዚኡ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ በውስተ ፡ ሕፅን ፡ ወምግብ ፡ ይከውን ፡ ለዘይሜግቦ ፡ ወውሳኬሰ ፡ ዲበ ፡ ስድማ ፡ ዘትዕግሥት ፡ ይደሉ ፡ ወለእመ ፡ ጠፍአ ፡ ውስተ ፡ እደሁ ፡ በግብር ፡ ክሡት ፡ ኢይደልዎ ፡ ዕዳ ። ወእመኒ ፡ ቆመ ፡ ስምዐ ፡ ጥያቄ ፡ ላዕለ ፡ አጥፍኦቱ ፡ ለውእቱ ፡ ይደ ልዎ ።

፩ሺ፪፻፳፭ ወእመ ፡ ሀለወ ፡ ምስሌሁ ፡ አብያጺ ፡ ወዘተአ ደወ ፡ ኪያሁ ፡ እምኔሆሙ ፡ ወነሥአ ፡ አው ፡

ከጠፋ ፡ በኋላ ፡ ስለሚገኝ ።

፩ሺ፪፻፳፩ መጠኑ ፡ ትንሽ ፡ ባይሆን ፡ ስለጠፋውም ፡ ገንዘብ ፡ መታጣት ፡ ብዙዎች ፡ ቢያዝኑ ፡ ለባ ለቤቱ ፡ መጠበቁን ፡ በማሰብ ፡ ሊወስደው ፡ ይገባል ። ሁኔታውንም ፡ ይመልከት ። መልኩ ንና ፡ ልኩን ፡ የሚያኖርበትን ፡ ቦታ ፡ ይወቅ ። በራሱ ፡ ሊያዳኝ ፡ ይገባዋል ። የሚለይበትን ፡ የመልኩን ፡ እኩሌታ ፡ ለምስክሮቹ ፡ ይናገር ። ለሰይጣን ፡ ለማሳቱ ፡ ምክንያት ፡ እንዳይሰጥ ፡ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ። (ኤፌ ፡ ፬ ፡ ፳፯) ።

፩ሺ፪፻፳፪ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ባገኘበት ፡ ቦታ ፡ የተሠራ ፡ ቢሆን ፡ እስከ ፡ ሰባት ፡ ሳምንት ፡ ድረስ ፡ በየሳ ምንቱ ፡ ሁሉ ፡ ወሬውን ፡ ይናገር ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በዙሪያው ፡ ላሉ ፡ ሰዎች ፡ በስብሰባዎች ፡ ቦታ ፡ ይኸውም ፡ እንደ ፡ አደባባይ ፡ እንደ ፡ ገቢያ ፡ ያለ ፡ ነው ። የሚያሳውቅ ፡ የመልኩን ፡ እኩሌታ ፡ ድርሀሞቹ ፡ የጠፉበት ፡ ማነው ፡ እያለ ፡ ያሳስብ ። ነገር ፡ ግን ፡ ምሳሌዋንና ፡ ሚዛ ኗን ፡ ወይም ፡ የኮረጆዋን ፡ ዓይነት ፡ ወይም ፡ የእንጥረኛ ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ ልብስ ፡ የጠፋበት ፡ ማነው ፡ ብሎ ፡ አይናገር ። ቀለሙንና ፡ መል ኩን ፡ እኳኋኑንም ፡ አይናገር ።

፩ሺ፪፻፳፫ የመጣ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ የጠፋውም ፡ ገንዘብ ፡ የእርሱ ፡ እንደሆነ ፡ ቢናገር ፡ ጥርጥርን ፡ እስኪ ያርቅ ፡ ድረስ ፡ የእርሱ ፡ እንደሆነ ፡ ከምልክቱ ፡ አብዛኛውን ፡ ቢጠቅስ ፡ በእርሷ ፡ ላይ ፡ ከመስ ክሩለት ፡ በኋላ ፡ የሚያውቁት ፡ ሰዎችም ፡ ባሉ በት ፡ ይመልሱለት ። ምስክር ፡ የሚሆንለት ፡ የታመነ ፡ ጨዋ ፡ ሰው ፡ ሊያመጣ ፡ ይገባዋል ። በቀጠሮው ፡ ባለቤቱ ፡ ባይደርስ ፡ ሊሠራበት ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ፪፻፳፬ ለአንዱ ፡ ባሪያ ፡ ቢሆን ፡ እውቀቱ ፡ አገልግ ሎቱ ፡ ገንዘብነቱ ፡ ለጌታው ፡ ይሆናል ። በሞግ ዚትና ፡ በመተዳደር ፡ ሥር ፡ ያለ ፡ ቢሆን ፡ ለሚ ያስተዳድረው ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ የትዕግ ሥትን ፡ ሥራ ፡ በቀጠሮ ፡ ላይ ፡ መጨመር ፡ ይገባል ። በታወቀ ፡ ሥራ ፡ በእጁ ፡ ቢጠፋ ፡ ዕዳ ፡ አይገባውም ። በማጥፋቱ ፡ የማስረጃ ፡ ምስክር ፡ ቢመሰከርበት ፡ ግን ለእርሱ ፡ ይገ ባዋል ።

፩ሺ፪፻፳፭ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ጓደኞች ፡ ቢኖሩ ፡ ከእነርሱ ፡ እርሱን ፡ ደፍሮ ፡ ያነሣው ፡ ወይም ፡ እንዲጠሰ

አዘዘ ፡ በንሚአቲ ፡ አልቦሙ ፡ ምንትኒ ፡ ክፍል ፡ በውስቴቱ ። ወዘኮነ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘሀለወ ፡ ቅድሜሁ ፡ አው ፡ በድኅሬሁ ፡ ወርእዮ ፡ ውእቱኬ ፡ ሰታፌሁ ፡ በዓቂብ ፡ ወበተዓውቆ ፡ በውስተ ፡ ዕድሜ ፡ ወበምልክና ፡ እምድኅረ ፡ ዝንቱ ።

፩ሺ፪፻፳፮ ወእመኒ ፡ ርእዮ ፡ ዘኢኮነ ፡ ቢጾ ፡ እምኔሆሙ ፡ ይስዶ ፡ ኀበ ፡ ምእመነ ፡ ፍትሕ ፡ ወእምድኅረ ፡ ዕድሜ ፡ ተዓውቆ ፡ ይግባእ ፡ ለዘረከቦ ። ወለእመ ፡ ኢኮነ ፡ ዘረከቦ ፡ እምሰብአ ፡ ሀገር ፡ ዘተረከበ ፡ በውስቴታ ፡ ንዋይ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ያንብሮ ፡ ኀበ ፡ ርእሰ ፡ ፍትሕ ፡ ወካልእ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ በኅርየት ፡ እመ ፡ ይተማህ ፡ ከመ ፡ ኢዕቀብ ፡ በዓስብ ፡ ወተዐውቆቱ ፡ እመ ፡ ይነሥእ ፡ ወውእቱ ፡ በእምጣነ ፡ ዕድሜ ፡ ወጻማ ፡ ወምጣኔ ፡ ሤጥ ።

፩ሺ፪፻፳፯ ወእመኒ ፡ ኮነ ፡ ዘተረከበ ፡ እምእንስሳ ፡ ዐቢያን ፡ እምአግማል ፡ ወአልሕምት ፡ ወአፍራስ ፡ ወአብቅልት ፡ ወአእዱግ ፡ ወለእመ ፡ ሀሎ ፡ ውስተ ፡ ምርዓይ ፡ እሙር ፡ ኢይደሉ ፡ ነሢአቱ ። ወእመሰ ፡ ኮነ ፡ ኍያዩ ፡ በውስተ ፡ ሀገር ፡ ኢይደሉ ፡ ኀዲጎቱ ፡ ወለእመ ፡ ተክህለ ፡ ነሢአቱ ፡ ኢያግብእዎ ፡ ዘእንበለ ፡ በሰምዐ ፡ ጥያቄ ፡ ወእመ ፡ እኮ ፡ በሰምዕ ፡ ርቱዕ ፡ እመሂ ፡ በ፪ቱ ፡ አው ፡ በ፫ቱ ፡ እምሰብእ ፡ እሙራን ።

፩ሺ፪፻፳፰ ወለእመሰ ፡ ኮነ ፡ እምእንስሳ ፡ ንኡሳን ፡ ዘከመ ፡ ጣዕዋ ፡ ሳሕም ፡ ወፈረስ ፡ ወአድግ ፡ ወገመል ፡ አው ፡ እምእባግዕ ፡ ወእስዋፍ ፡ ወዘ ይመስሎ ፡ ለዝንቱ ፡ ወተረከበ ፡ በባሕቲቱ ፡ ኢይደሉ ፡ ኀዲጎቱ ፡ እመ ፡ ይትክህል ፡ ነሢአቱ ። ወነሢኢሁኒ ፡ ይኅረይ ፡ እመ ፡ ያስተዋስእ ፡ ሳዕሌሁ ፡ በዕድሜ ፡ ተዓውቆቱ ፡ ወለእመ፡ ኮነ ፡ ውእቱ ፡ ይሚጡ ፡ ለመሳኪሁ ፡ እመ ፡ አኮ ፡ ለእመ ፡ ኮነት ፡ ሎቱ ፡ ዓስብ ፡ አው ፡ እምንዋዩ፡ ይደልዎ ፡ ሊቃሕ ፡ ለመሳኪሁ ። ወለእመ ፡ በጽሐ ፡ መሳኪሁ ፡ ይንሣእ ፡ እምኔሁ ፡ ዘአስተዋስአ ፡ ሎቱ ፡ ወዓስበ ፡ ዓቂቦቱ ፡ ወአሁቆቱ ፡ ለእመ ፡ ኀረየ ፡ ወያግብእ ፡ ሎቱ ፡ ምስለ ፡ ዘተሞ ለደ ። ወለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ከመ ፡ ይሚጦ ፡ በትእዛዘ ፡ ፈታሒ ፡ እምድኅረ ፡ ስብዓ ፡ ወይጽናሕ ፡ በእንተ ፡ ተዓውቆቱ ፡ እድሜ ፡ እሙረ ። ወእም ድኅሬሁ ፡ ይደልዎ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይሥራዕ ፡



ዱት ፡ ያዘዘ ፡ በውስጡ ፡ ምንም ፡ ድርሻ ፡ የላ ቸውም ። ከእነርሱ ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ በፊቱ ፡ ወይም ፡ በኋላው ፡ ያለ ፡ ቢያየው ፡ በመጠበ ቅና ፡ በመታወቅ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በቀጠሮና ፡ በገንዘብ ፡ ተሳታፊው ፡ እርሱ ፡ ነው ።

፩ሺ፪፻፳፮ ከእነርሱ ፡ ጓደኛው ፡ የያይደለ ፡ ሰው ፡ ቢያየው ፡ በፍርድ ፡ ወይታመነ ፡ ዳኛ ፡ ይውሰደው ። ከም ርምሩ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ላገኘው ፡ ሰው ፡ ይሁን ። ያገኘው ፡ ሰው ፡ ገንዘቡ ፡ ከተገኘበት ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ወገን ፡ ባይሆን ፡ በዳኛ ፡ ዘንድ ፡ ወይም ፡ በሌላው ፡ ዘንድ ፡ ሊያኖሩት ፡ ይገባል ። በኪራይና ፡ በምርመራው ፡ ይጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ ቢተጋ ፡ በምርጫ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ። ቢቀበለ ውም ፡ ይኸውም ፡ በጊዜና ፡ በድካም ፡ በዋጋም፡ ልክ ፡ ነው ።

፩ሺ፪፻፳፯ የተገኘው ፡ ገንዘብ ፡ ከታላላቆቹ ፡ እንስሳት ፡ ወገን ፡ ከግመሎችና ፡ ከላሞች ፡ ከፈረሶችና ፡ ከበቅሎች ፡ ከአህዮችም ፡ ቢሆን ፡ በታወቀ ፡ መሰማሪያ ፡ ውስጥ ፡ ቢኖር ፡ መውሰድ ፡ አይ ገባም ። በሀገሩ ፡ ውስጥ ፡ የሚኮበልል ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ሊተውት ፡ አይገባም ። መያዝ ፡ ቢቻልም፡ በማስረጃ ፡ ምስክር ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አይመል ሱለት ። ያም ፡ ባይሆን ፡ በሚገባ ፡ ምስክር ፡ ከታ ወቁ ፡ ሰዎች ፡ ወገን ፡ በሁለት ፡ ወይም ፡ በሦስት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ።

፩ሺ፪፻፳፰ ከታናናሽ ፡ እንስሳትም ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ላም ፡ ጥጃ ፡ እንደ ፡ ፈረስ ፡ ግልገል ፡ እንደ ፡ አህያ ፡ ውርንጫ ፡ እንደ ፡ ግመል ፡ ወሳብሬ ፡ ወይም ፡ ከበጎችና ፡ ከወፎች ፡ ይህንም ፡ ከሚመ መስለው ፡ ወገን ፡ ብቻውን ፡ ቢገኝ ፡ መያዝ ፡ ከተቻለ ፡ ሊተዉት ፡ አይገባም ። ያገኘውም ፡ ሰው ፡ በሚመሰክርበት ፡ ጊዜ ፡ ለእርሱ ፡ ሊያ ወጣጣ ፡ ቢወድ ፡ ያወጣጣ ። ለባለቤቱ ፡ የሚ በጀው ፡ ከሆነ ፡ ያም ፡ ባይሆን ፡ ከራሱ ፡ ወይም፡ ከገንዘቡ ፡ ኪራይ ፡ ያለው ፡ ቢሆን ፡ ለባለቤቱ ፡ ብድር ፡ ይገባዋል ። ባለቤቱ ፡ ቢደርስ ፡ ያወ ጣጣለትን ፡ የመጠበቁንና ፡ የማስመርመሪ ያውን ፡ ዋጋ ፡ ከእርሱ ፡ ይቀበል ። ቢወድ ፡ ከርቢው ፡ ጋር ፡ ይመልስለት ። ከሳምንቱ ፡ በኋ ላ ፡ በዳኛ ፡ ትእዛዝ ፡ ሊሸጥ ፡ ቢወድ ፡ ስለማስመ ርመሩ ፡ የታወቀ ፡ ጊዜ ፡ ይቆይ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በዋጋ ፡ ሊሠራበት ፡ ይገባዋል ። በዋጋውም ፡

ውስተ ፡ ሜጥ ፡ ወይደሉ ፡ ከመ ፡ ያማየጥ ፡ በሚጠ ፡ ዚአሁ ፡ ጉልተ ፡ ለጽኑሳን ፡ ወያቅድም ፡ ሶቤሃ ፡ እምኔሁ ፡ ውሂበ ፡ ለምንዱባን ፡ በዘአንበረ ፡ ሎሙ ፡ በእንተ ፡ ዘይትነኖል ፡ ቦቱ ፡ ያም ፡ አው ፡ ይመጽውት ፡ ለጽኑሳን ፡ ወእመቦ ፡ ፩ዱ ፡ ዘተጸንሰ ፡ ሎቱ ፡ ያድልወ ።

፩ሺ፪፻፳፱ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘተረክበ ፡ ዘይማስን ፡ ፍጡነ ፡ ይደሉ ፡ ሠይጦቱ ። ለእመ ፡ ይትከሀል ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ መብልዐ ፡ ይብልዕዎ ። ወእም ከመ ፡ በጽሐ ፡ ፩ዱ ፡ ወአጠየቀ ፡ እምድኅረ ፡ ዕድሜ ፡ አእምሮ ፡ ከመ ፡ ዘጠፍአ ፡ ዚእሁ ፡ ውእቱ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ህልወ ፡ ኅበ ፡ ዘረከቦ ፡ ያግብዕ ፡ ሎቱ ፡ ወእመኒ ፡ ሤጠ ፡ ያግብእ ፡ ሤጦ ። ወለእመ ፡ ተመገበ ፡ ቦቱ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ባዕለ ፡ ያደልዎ ፡ ከመ ፡ ያግብእ ፡ ቴመተ ፡ ንዋይ ፡ ወእመኒ ፡ ኮነ ፡ ጽኑሰ ፡ ወተጸንሰ ፡ በገሃድ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ያግብእ ፡ ዘተርፈ ፡ ወእመሰ ፡ ኢተርፈ ፡ ምንትኒ ፡ እምንዋይ ፡ ኢየኀዝዎ ፡ በምንትኒ ።

፩ሺ፪፻፴ ወእመኒ ፡ ኮነ ፡ ዘወሀበ ፡ ኪያሁ ፡ በእንተ ፡ ጽድቅ ፡ ይኅረይ ፡ መላኪሁ ፡ እመኒ ፡ ከመ ፡ ይኩኖ ፡ ዓስበ ፡ ጽድቅ ፡ አው ፡ ከመ ፡ ያግብእ ፡ ሎቱ ፡ እመሂ ፡ ኮለንታሁ ፡ አው ፡ መንፈቀ ፡ ዚአሁ ፡ ለእመ ፡ ተረክበ ፡ ለሊሁ ፡ አው ፡ ሤጠ ፡ ዚአሁ ። ወቃልኒ ፡ ቃለ ፡ ነሣኢ ፡ በኵሉ ፡ ዘያትኃእዞ ፡ ቦቱ ፡ ምስለ ፡ መላኪ ፡ ዘእንበለ ፡ ዳእሙ ፡ ለእመ ፡ አቀመ ፡ መላኪ ፡ ስምዐ ፡ ጥዩቀ ፡ በተኃእዞቱሙ ። ወኵሉ ፡ ዘተረክበ ፡ ከመ ፡ እንተ ፡ ማኅፀንት ፡ ውእቱ ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ ዘረከቦ ።

፩ሺ፪፻፴፩ ክፍል ፡ ዳግም ፡ በእንተ ፡ ሕፃን ፡ ዘተነጥአ ፡ ወተረክበ ፡ ወዘሂ ፡ ረከቦ ፡ ያግእዞ ፡ እስመ ፡ ጥንተ ፡ ፍትሕ ፡ ውእቱ ፡ እምደቂቀ ፡ መሃይምናን ፡ ወይደልዎ ፡ ግዕዛን ፡ ወውእቱ ፡ ቀዳማዊ ፡ ዘእንበለ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ መካን ፡ ዘተረክበ ፡ ቦቱ ፡ አልቦ ፡ ውስቴቱ ፡ መሃይምናን ፡ ወነገሩ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ እምውሉዶሙ ፡ አው ፡ ለእመ ፡ ኮኑ ፡ መሃይምናን ፡ ውኁዳነ ፡ ይሕትትዎሙ ።

፩ሺ፪፻፴፪ ወለእመ ፡ ተረክበ ፡ ምስሌሁ ፡ ንዋይ ፡ ምንትኒ ፡ ወእመሂ ፡ ንቡረ ፡ ኀበ ፡ ገቦሁ ፡ ቅሩበ ፡ ይፍትሖ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ደልው ፡ ወያስተዋስእ ፡ ላዕሌሁ ፡ እምኔሁ ፡ በትእዛዘ ፡ ፈታሒ ፡



ለተቸገሩ ፡ ሰዎች ፡ ጉልት ፡ ሊገዛ ፡ ይገባል ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ደም ፡ ስለሚደርቅበት ፡ ባኖረላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ለተቸገሩ ፡ ሰዎች ፡ ከእርሱ ፡ ያስቀድም ፡ ፡ ወይም ፡ ለድሆች ፡ ይመጽውተው ። አንድ ፡ የተቸገረ ፡ ቢኖር ፡ ለርሱ ፡ ያድሉለት ።

፩ሺ፪፻፳፱ የተገኘው ፡ ፈጥኖ ፡ የሚጠፋ ፡ ቢሆን ፡ ከተቻለ ፡ ሊሸጡት ፡ ይገባል ። የሚበላ ፡ ቢሆን ፡ ይብሉት ። ከምርመራው ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ አንዱ ፡ ደርሶ ፡ የጠፋው ፡ ገንዘብ ፡ የእርሱ ፡ እንደሆነ ፡ ቢያስረዳ ፡ በአገኘው ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ ያለ ፡ ቢሆን ፡ ይመልስለት ። ቢሸጠውም ፡ ዋጋውን ፡ ይመልስ ። ቢበላውም ፡ ባለጸጋ ፡ ከሆነ ፡ የገንዘቡን ፡ ዓይነት ፡ ሊመልስ ፡ ይገባዋል ። ችግረኛ ፡ ቢሆን ፡ ችግሩም ፡ በግልጽ ፡ ቢሆን ፡ የተረፈውን ፡ ሊመልስ ፡ ይገባዋል ። ከገንዘቡ ፡ ምንምን ፡ ባይተርፍ ፡ ግን ፡ በምንም ፡ አይያዙት ።

፩ሺ፪፻፴ ስለ ፡ ጽድቅ ፡ እርሱን ፡ የሰጠ ፡ ቢሆንም ፡ የጽድቅ ፡ ዋጋ ፡ ይሆንለት ፡ ዘንድ ፡ ወይም ፡ መላውን ፡ ወይም ፡ እኩሌታውንም ፡ ቢሆን ፡ ዓይነቱ ፡ ወይም ፡ ዋጋው ፡ ቢገኝ ፡ ይመልስለት ፡ ዘንድ ፡ ባለቤቱ ፡ ይምረጥ ። ከባለቤቱም ፡ ጋር ፡ በሚከራከርበት ፡ ሁሉ ፡ ቃሉ ፡ የአግኚው ፡ የባለይዞታው ፡ ቃል ፡ ነው ። ባለቤቱ ፡ በክርክራቸው ፡ የማስረጃ ፡ ምስክር ፡ ቢያስመሰክር ፡ ነው ፡ እንጂ ። የተገኘ ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ ባገኘው ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ አደራ ፡ ነው ።

፩ሺ፪፻፴፩ ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ጠፍቶ ፡ ስለተገኘ ፡ ሕፃን ፡ ይናገራል ። ያገኘው ፡ ሰው ፡ ነፃ ፡ ያወጣው ፡ ከአማንያን ፡ ልጆች ፡ ወገን ፡ ከሆነ ፡ የፍርድ ፡ መጀመሪያ ፡ ነውና ፡ ነፃነትም ፡ ይገባዋል ። ይኸውም ፡ መጀመሪያ ፡ ነው ። የተገኘበት ፡ በውስጡ ፡ አማንያን ፡ የሌሉበት ፡ ቦታ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ከልጆቻቸው ፡ ወገን ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ ምእመናን ፡ ጥቂቶች ፡ እንደሆኑ ፡ ቢናገሩ ፡ ይመርምሯቸው ።

፩ሺ፪፻፴፪ የታሠረ ፡ ወይም ፡ በአጠገቡ ፡ ቀርቦ ፡ የተቀመጠ ፡ ገንዘብ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ቢገኝ ፡ ለእርሱ ፡ እንደሚገባው ፡ ይፍረዱ ። በዳኛ ፡ ትእዛዝ ፡ ከዚሁ ፡ ለእርሱ ፡ ያውጣጣ ፡ በእርሱ ፡ ላይና ፡

ወይደሉ ፡ ከመ ፡ ያስምዑ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወላዕለ ፡ ዘተረክበ ፡ ምስሌሁ ። ወለእመ ፡ ኢተረክበ ፡ ምስሌሁ ፡ ምንትኒ ፡ ንዋይ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘረከቦ ፡ ባዕለ ፡ ወከሃሌ ፡ ላዕለ ፡ መግቦቱ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይንሥእ ፡ ወይሕፅኖ ፡ ወእመ ፡ አኮሰ ፡ ይንሥእ ፡ መጋቤ ፡ ንዋየ ፡ ምጽዋት ፡ በትእዛዘ ፡ ፈታሒ ፡ ወየሀቦ ፡ ለዘየሐፅኖ ፡ እመኒ ፡ እምኅበ ፡ ዘየሐፅኖ ፡ ለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ወእመ ፡ አኮሰ ፡ ያስተዋፅእ ፡ ላዕሌሁ ፡ እምንዋየ ፡ ምጽዋት ፡ ዘይትፈቀድ ፡ ለተሐፅኖቱ ፡ ወትምህርቱ ፡ ግብረ ፡ እድ ።

፩ሺ.፪፻፴፫ ወከማሁ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘረከቦ ፡ ገብረ ፡ ምእመን ፡ አው ፡ ኢአማኒ ፡ ዘኢያቅደመ ፡ ብሂለ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ውሉዶሙ ፡ ለእለ ፡ ኢየአምኑ ፡ ወዘይቤ ፡ ዚአየ ፡ ውእቱ ፡ ወአቀመ ፡ ሰምዐ ፡ ጥያቄ ፡ የሀብዎ ፡ ኪያሁ ፡ በከነ ፡ ከዊኖ ፡ ወይደልዎ ፡ ለዘየሐፅኖ ፡ ከመ ፡ ያንብሮ ፡ ኅቤሁ ፡ ከመ ፡ ወልዱ ፡ ወይምሀሮ ፡ ግብረ ፡ እድ ፡ እንተ ፡ ይፈቅድ ፡ ኪያሃ ፡ ለውሉደ ፡ ዚአሁ ፡ አው ፡ ዘተከሥተ ፡ ሎቱ ፡ እምልቡናሁ ፡ ዘይበቍዖ ፡ ሎቱ ፡ በአምጣነ ፡ ተሳሕዮተ ፡ ጠባይዒሁ ፡ ወይትዌለዎ ፡ በዝንቱ ፡ ኅበ ፡ ዘይጸንን ፡ መንገሌሁ ፡ ወዘይፈቅዶ ፡ ወይንሥእ ፡ በሰብዎቱ ፡ እምኔቱ ፡ ወይግበር ፡ በከመ ፡ ይደሉ ፡ ለሃይማኖቱ ።

፩ሺ.፪፻፴፬ ክፍል ፡ ዘይትለዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ወዘሂ ፡ አግብአ ፡ ጕያዬ ፡ እምኅበ ፡ ዘጕየ ፡ እምኔሁ ፡ እመሂ ፡ ወልዶ ፡ አው ፡ ገብረ ፡ ዚአሁ ፡ አው ፡ ዘተሐተ ፡ ምግበ ፡ ዚአሁ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ የሀቦ ፡ ዘወሀቦ ፡ በእንቲአሁ ፡ እመ ፡ ለሊሁ ፡ የኀሪ ፡ እመ ፡ የኀድጎ ፡ በእንተ ፡ ጽድቅ ፡ ወእመ ፡ ይንሥእ ፡ እምኔሁ ። ወዓስቡኒ ፡ በአምጣነ ፡ ዓማሁ ፡ ወበአምጣነ ፡ ፍኖት ፡ ዘሀሎ ፡ ማእከለ ፡ ፪ቱ ፡ መካናት ፡ እንተ ፡ አግብአ ፡ ኅቤሁ ፡ እምኔሁ ፡ ወመጠነ ፡ ዕድሜ ፡ እምአመ ፡ ተኀጥአ ፡ እስከ ፡ ያገብአ ። ወለእመ ፡ ጕየ ፡ እምኅበ ፡ ዘአግብአ ፡ ኢይደልዎ ፡ ዕዳ ፡ አላ ፡ ይደልዎ ፡ ያስምዕ ፡ ላዕለ ፡ ነፍሱ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ነሥአ ፡ ከመ ፡ ያግብአ ፡ ኅበ ፡ እግዚኡ ። ወእመኒ ፡ ኮነ ፡ ዘጕየ ፡ ገብረ ፡ አው ፡ እኑዘ ፡ ረድዮ ፡ ወውሂብ ፡ ላዕለ ፡ ዘነሥአ ፡ በእንተዘ ፡ ይከውን ።

፩ሺ.፪፻፴፭ ክፍል ፡ ወዘነገደ ፡ ወኢተአምረ ፡ መካኑ ፡ እመ ፡ ሕያው ፡ ውእቱ ፡ አው ፡ አልቦ ፡ ወተረክበ ፡ ሎቱ ፡ ንዋይ ፡ ያብጽሕዎ ፡ ኅበ ፡ ፈታሒ ፡



ከእርሱ ፡ ጋር ፡ በተገኘው ፡ ላይ ፡ ሊያዳኙ ፡ ይገባል ። ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ምንም ፡ ገንዘብ ፡ ባይገኝ፡ ያገኘው ፡ ሰው ፡ ባለጸጋና ፡ እርሱን ፡ መመገብ ፡ የሚቻለው ፡ ቢሆን ፡ ወስዶ ፡ ያሳድገው ፡ ዘንድ ፡ ተገባው ። ያለዚያ ፡ ግን ፡ በምጽዋት ፡ ገንዘብ ፡ የተሾመው ፡ ሰው ፡ በዳኛ ፡ ትእዛዝ ፡ ይውሰደው ። ከሚያሳድገውም ፡ ዘንድ ፡ ቢሆን፡ ቢወድ ፡ ለሚያሳድገው ፡ ይስጠው ። ይህም ፡ ባይሆን ፡ ግን ፡ ለሚያድግበትና ፡ ተግባረ ፡ እድ ለሚማርበት ፡ የሚያሻውን ፡ ከምጽዋት ፡ ገንዘብ ፡ ያወጣጣ ። እንዲሁም ፡ ያመነ ፡ ወይም ፡ ያላመነ ፡ ባሪያ ፡ ያገኘ ፡ሰው ፡ ወይም ፡ ካላመኑ ፡ ሰዎች ፡ ልጆች ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መናገርን ፡ ያላስቀደመ ፡ የእኔ ፡ ነውም ፡ የሚል ፡ የማስረጃ፡ ምስክርም ፡ የጠራ ፡ ቢሆን ፡ የሆነ ፡ ሁኖ ፡ እርሱን ፡ ይስጡት ። ለአሳዳጊው ፡ እንደ ፡ ልጁ ፡ አድርጎ ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ሊያኖረው ፡ ይገባዋል ። ለልጆቹ ፡ የሚሻውን ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ ለባሕርዩ ፡ እንደሚስማማው ፡ መጠን ፡ ለእርሱ ፡ የሚጠቅመውን ፡ ከልቡናው ፡ የተገለጸለትን ፡ ያስተምረው ። ወደ ፡ እርሱ ፡ በሚያዘነብልበት ፡ ገንዘብ ፡ በሚወደው ፡ በዚህ ፡ ይከባከበው ። እምነቱንም ፡ በማስተዋል ፡ ይያዘው ። ለሃይማኖቱ ፡ እንደሚገባ ፡ ያድርግ ።

፩ሺ.፪፻፴፬ ክፍል ። ከዚህ ፡ የሚከተለውን ፡ ይናገራል ። ኰብላዩን ፡ ከኰበለለበት ፡ የመለሰ ፡ ሰው ፡ ልጁንም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ባሪያውን ፡ ወይም ፡ ከእርሱ ፡ አስተዳደር ፡ ሥር ፡ ያለውን ፡ ስለ ፡ ጽድቅ ፡ ቢተወውና ፡ ከእርሱም ፡ ቢወስደው ፡ እርሱ ፡ መርጦ ፡ የሰጠውን ፡ ገንዘብ ፡ ሊሰጥ ፡ ይገባዋል ። ዋጋውም ፡ በድካሙ ፡ልክና ፡ ከእርሱ ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ በመለሰበት ፡ በሁለቱ ፡ ቦታዎች ፡ መካከል ፡ ባለ ፡ ጎዳና ፡ ልክ ፡ ከጠፋበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እስከሚመለሰበት ፡ ጊዜ ፡ ልክ ፡ ነው ። ከመለሰበት ፡ ቦታ ፡ ቢጠፋ ፡ ዕዳ ፡ አይገባውም ። ወደጌታው ፡ ሊመልሰው ፡ እርሱ እንደ ፡ ወሰደው ፡ ለራሱ ፡ ሊያስመሰክር ፡ ይገባዋል ፡ እንጂ ። የጠፋው ፡ ገንዘብ ፡ ባሪያ ፡ ወይም የሚከፈል ፡ መያዣና ፡ ሰጦታ ፡ ቢሆን ፡ ለያዘው ፡ ሰው ፡ በመያዣ ፡ ይሆናል ።

፩ሺ.፪፻፴፭ ክፍል ፡ እሩቅ ፡ ሀገር ፡ የሄደ ፡ ሰው ፡ ቦታውም ፡ ባይታወቅ ፡ ሕያውም ፡ እንደሆነ ፡ ወይም እንዳልሆነ ፡ ገንዘቡ ፡ ቢገኝለት ፡ ወደዳኛ ፡

ወፈታሒ ፡ ይሚም ፡ ላዕሌሁ ፡ መጋቢ ፡ ምእመን ፡ ዘይበቁዕ ፡ እመኒ ፡ በእንተ ፡ ጸድቀ ፡ ፈቂዶ ፡ እው ፡ በተዓስቦ ፡ ከመ ፡ ይስቀብ ፡ ንዋየ ፡ ወይንግሥ ፡ ለዘለቅሖ ፡ ወያስተዋፅኦ ፡ ላዕለ ፡ ሰብእ ፡ ወይፍዲ ፡ ተለቅሖቶ ።

፩ሺ.፪፻፴፮ ወመፍትው ፡ ከመ ፡ ያስተጸንዕ ፡ ዘሐይሰ ፡ በቅድመ ፡ ሰማዕት ፡ ወጸሐፊ ፡ ቀሪክ ፡ ወእምከመ ፡ ኀለፈ ፡ ብዙኀ ፡ መዋዕለ ፡ እምዘተረከበ ፡ ይፍትሑ ፡ ፍትሐ ፡ ማእከለ ፡ እለ ፡ ይደልዎሙ ። ለእመ ፡ ኢኮነ ፡ ሕያወ ፡ በዓለ ፡ ንዋይ ፡ ይትከፈሉ ፡ ወይረሱ ፡ ድልወ ፡ ሎሙ ፡ ለእለ ፡ ረከቡ ፡ እሚሃ ፡ አምድኅረ ፡ ተቀብጸ ፡ እስከ ፡ ይትረከብ ፡ ኢይትከፈሉ ፡ ዘረከብዎ ፡ ለንዋይ ፡ ኢይረሱ ፡ ወኢያውርሱ ።



ያድርስ ፡ ዳኛውም ፡ የሚጠቅም ፡ ታማኝ ፡ ሹም ፡ ይሹምለት ። ስለ ፡ ጽድቅ ፡ ወዶ ፡ ወይም በዋጋ ፡ ቢሆን ፡ ገንዘቡን ፡ ይጠብቅ ፡ ዘንድ ። ያበደረውንም ፡ ይቀበልለት ። ለቤቱ ፡ ሰብእ ቱም ፡ ያጠጣጣ ። የተበደረውንም ፡ ይክፈል ።

፩ሺ.፪፻፴፮ በምስክር ፡ ፊትና ፡ ደብዳቤ ፡ በመጻፍ ፡ ያደ ሰውን ፡ ሊያጸና ፡ ይገባዋል ። ከተገኘ ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ካለፈ ፡ መውረስ ፡ በሚገባቸው ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ፍርድ ፡ ይፍረዱ ። ባለገን ዘቡ ፡ ሕያው ፡ ባይሆን ፡ ያንጊዜ ፡ ላገኙት ፡ ሊካፈሉና ፡ ሊወርሱ ፡ ይገባቸዋል ። ተስፋ ፡ ከተቈረጠ ፡ በኋላ ፡ ገንዘቡን ፡ ያገኙት ፡ አይካ ፈሉ ። አይውረሱ ። አያውርሱም ።

## አንቀጽ ፡ ፵ወ፪ዱ ።

በእንተ ፡ ዘይእኅዝ ፡ በንዋዩ ።

፩ሺ.፪፻፴፯ ሥርዓትስ ፡ በዝንቱ ፡ አንቀጽ ፡ ይትከፈል ፡ ኀበ ፡ ፪ቱ ፡ ክፍል ። ንዋይ ፡ ዘይእኅዝ ፡ ቦቱ ፡ ወአጽሕፎቱ ፡ ወስሙ ፡ ለዘይእኅዝ ፡ ወለዘይ እኅዙ ፡ ሎቱ ፡ ወዘይእኅዙ ፡ ኪያሁ ፡ ወዘይእኅ ዝዎሚ ።

፩ሺ.፪፻፴፰ ቀዳሚ ፡ በእንተ ፡ ትእዛዝ ፡ ወጽሕፈቱሂ ፡ ጠስ ፡ ፳ወ፩ዱ ። ንዋይሰ ፡ ዘይእኅዝ ፡ ቦቱ ፡ በምክር ፡ ድልው ፡ ውእቱ ፡ ዘይፈቅዶ ፡ ሰብእ ፡ ከመ ፡ ይመጽው ፡ እምንዋዩ ፡ እምድኅረ ፡ ሞቱ ፡ ዘተርፈ ፡ እምነ ፡ ዘያወርስ ፡ ወይደሉ ፡ ገቢሮቱ ፡ በከመ ፡ ቃሎሙ ፡ ለነቢያት ፡ ወለሐ ዋርያት ። እስመ ፡ ኢሳይያስ ፡ ነቢይ ፡ ይቤሎ ፡ ለሕዝቅያስ ፡ ንጉሥ ፡ በቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ አዝዝሙ ፡ ለደቂቅከ ፡ እስመ ፡ እንተ ፡ ትመውት ። ወለሐዋርያትኒ ፡ ብዙኃን ፡ እምኔ ሆሙ ፡ አዘዙ ፡ እመኒ ፡ በዘይመጽውትዎ ፡ ለጽ ኑሳን ፡ ወቦ ፡ ዘይትዌልቱ ፡ ኪያሁ ፡ ወየዐብ ዮሙ ፡ ለእለ ፡ ቦሙ ፡ ተጽናስ ፡ ወለእጓለ ማውታ ሳን ።

፩ሺ.፪፻፴፱ ወለዘሞተኒ ፡ ባሕቲቱ ፡ ይከውኖ ፡ ከመ ፡ የአ ዝዝ ፡ በጽድቅ ፡ ወእልባቲ ፡ በቀኑዓት ፡ ለት እዛዝ ፡ እንዘ ፡ ሀለወ ፡ ሕያወ ፡ እግዚእ ፡ ከመ ፡ ቃለ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ።

፩ሺ.፪፻፵ ጠስ ፡ ፳ወ፩ዱ ፡ ወእዝዘሰ ፡ ይኩን ፡ በጽሒፍ ፡

## አንቀጽ ፡ ፵፪ ።

በገንዘቡ ፡ ስለሚያዝዝ ፡ ይናገራል ።

፩ሺ.፪፻፴፯ ሥርዓትስ ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ከአምስት ፡ ክፍል ፡ ይከፈላል ። የሚያዝዝበት ፡ ገንዘብና ፡ አጻጻፉ ፡ የሚያዘው ፡ ሰው ፡ ስም ፡ የሚያዝ ለት ፡ ሰው ፡ እርሱን ፡ የሚያዝዙትም ፡ ትእዛዝ ፡ የሚያዝዙትም ፡ ሰው ፡ ናቸው ።

፩ሺ.፪፻፴፰ መጀመሪያ ፡ ስለ ፡ ትእዛዙና ፡ ስለአጻጻፉም ፡ ይናገራል ። ጠስ ፡ ፳፩ ። በተገባ ፡ ምክር ፡ የሚ ያዝዝበት ፡ ገንዘብስ ፡ ከሚያወርሰው ፡ የተረፈ ውን ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ይመጸውት ፡ ዘንድ ፡ ሰው ፡ የሚሻው ፡ ነው ። እንደ ፡ ነቢያትና ፡ እንደ ፡ እስተዋዮች ፡ ሰዎች ፡ ቃል ፡ መሥራቱ ፡ ይገባል ። ነቢዩ ፡ ኢሳይያስ ፡ በልዑል ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ቃል ፡ ንጉሥ ፡ ሕዝቅያስን ፡ አንተ ፡ ትሞታለህና ፡ ልጆችህን ፡ እዘዛቸው ፡ ብሎታ ታልና ። (፪ ፡ ነገ ፡ ፳ ፡ ፩) ።ከእስተዋዮችም ፡ ብዙዎቹ ፡ ለችግረኞች ፡ በሚመጸውቱትም ፡ ቢሆን ፡ አዘዙ ። የጐለቱትም ፡ አለ ። ችግር ፡ ላለባቸውና ፡ ላልተቸገሩትም ፡ ሰጡቸው ።

፩ሺ.፪፻፴፱ ለሟች ፡ ብቻ ፡ በእውነት ፡ ሊያዝዝ ፡ ይገ ባዋል ። አዛዡም ፡ በሕይወቱ ፡ ሥጋ ፡ ሳለ ፡ ትእ ዛዝ ፡ እንደ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ ቃል ፡ ጥቅም ፡ የላትም ። (ሰብ ፡ ፱ ፡ ፲፯) ።

፩ሺ.፪፻፵ ጠስ ፡ ፳፩ ። ትእዛዝ ፡ ግን ፡ በጽሕፈትም ፡

ወዘእንበለ ፡ ጽሒፍ ፡ በትእዛዝ ፤ ወዘእንበለ ፡ ትእዛዝ ፡ ለዘያማኀፅንዎ ።

፩ሺ.፪፻፺፩ ወእንተሰ ፡ በጽሒፍ ፡ ትትፌጸም ፡ በጽሒፈ ፡ ጸሓፊ ፡ አው ፡ በጽሒፈ ፡ ዘያማኀፅንዎ ፡ አው ፡ በጽሒፈ ፡ አዛዚ ፡ ወሀልዎተ ፡ ሰማዕታት ፡ ጊዜ ፡ ተጽሕፎታ ፡ እንተ ፡ ትትላጸቅ ፡ በእሐቲ፡ ጽሒፍ ። ወሰምዐ ፡ ይኩኑ ፡ በውስቴታ ፡ እለ ፡ ጉቡአን ፡ እሙንቱ ፡ ወይኩን ፡ ኍልቆሙ ፡ ፯ተ አው ፡ ፭ተ ፡ ለእመ ፡ ይትከሀል ፡ ወእመ ፡ አኮሰ ፡ ፫ተ ፡ አው ፡ ፪ተ ።

፩ሺ.፪፻፺፪ ወይጽሐፍ ፡ ዘይኤዝዝ ፡ ውስቴታ ፡ ክዋኔ ፡ ዚአሃ ፡ ወእማሬ ፡ ዕለታ ፡ ወአስማተ ፡ ወራስያኒሁ ፡ በጽሕፈተ ፡ እዴሁ ፡ እመ ፡ ጸሓፊ ፡ ውእቱ ፡ ወይበል ፡ ናሁ ፡ አነ፡ ረሰይክዎሙ ፡ ለእገሌ ፡ ወለእገሌ ፡ ወራስያነ ፡ ዚአየ ። ወእመሰ ፡ ኢኮነ ፡ ጸሐፌ ፡ ይጽሐፉ ፡ እለ ፡ ይከውኑ ፡ ሰምዐ ፡ ህየንቴሁ ፡ አስማቲሆሙ ፡ ለወራስያኒሁ ። ወይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ሰምዐ ፡ በውስቴታ ፡ ጸሓፌ ፡ ዚአሃ ፡ ወአዛዚ ፡ ዘገብረ ፡ ውስቴታ ፡ ወለዘሰ ፡ ይኤዝዙ ፡ ሎቱ ፡ አልቦ ። ወይኩን ፡ ዓዲ ፡ ጽሕፈቶሙ ፡ ለወራስያን ፡ በውስቴታ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ሠመርነ ፡ በዘተጽሕፈ ፡ በውስቴታ ።

፩ሺ.፪፻፺፫ ወእንተሰ ፡ ትከውን ፡ ዘእንበለ ፡ ጽሒፍ ፡ ኢትኩን ፡ በተናሕልዎ ፡ ጽሕፈት ፡ ወእንተሰ ፡ ትከውን ፡ ዘእንበለ ፡ መጽሐፍ ፡ እስመ ፡ ትከውን ፡ በእንተ ፡ ግብረ ፡ ጽሕፈት ፡ ወኢይደሉ ፡ ዘእንበለ ፡ ሰማዕት ፡ ወኢይትከሀል ፡ ዘእንበለ ፡ በህላዌ ፡ ሰማዕት ። መክ ፡ ፲ወ፩ዱ ፡ ወኢይደሉ ከመ ፡ ይኩን ፡ ትእዛዝ ፡ በጽሒፈ ፡ ተአዛዚ ።

፩ሺ.፪፻፺፬ መክ ፡ ፺ወ፬ቱ ፡ ፲ወ፯ቱ ፡ ጠስ ፡ ፺ወ፪ቱ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ያውዕኡ ፡ ቅድመ ፡ እምንዋይ ፡ ዘነደገ ፡ አዛዚሃ ፡ ዘይትፈቀድ ፡ ለግንዘቱ ፡ ወለክራይያን ፡ ወለመቃብሩ ፡ ወለፈድየ ፡ ዕዳ ፡ ዘላዕሌሁ ፡ አው ፡ ጸባሕት ፡ ወለእመ ፡ አልቦ ፡ ዘእንበሌሃ ።

፩ሺ.፪፻፺፭ ጠስ ፡ ፴ወ፯ቱ ፡ ወኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይትኀሠሥ ፡ በውስተ ፡ ዘተአዘዘ ፡ ቦቱ ፡ እምቅድመ ፡ ተሰዐ ፡ መዋዕል ፡ ወትእዛዝሰ ፡ ትበርዕ ፡ በቃል ፡ ርቱዕ ፡ ለእመ ፡ ኢገብረ ፡ ኪያሃ ፡ እመኒ ፡ በገቢር ፡ ከመ ፡ ሠይጥ ፡ ወእግዕዞ ፡ እምግብርናት ፡ ወአውስቦ ፡ አመት ፡ ወፈደ

ያለ ፡ ጽሕፈትም ፡ በትእዛዝ ፡ ያለ ፡ ትእዛዝም ፡ አደራ ፡ ላስጠበቁት ፡ ሰው ፡ ይሁን ።

፩ሺ.፪፻፺፩ በጽሑፍ ፡ የምትፈጸመውስ ፡ በጸሓፊ ፡ ጽሕፈት ፡ ወይም ፡ ባደራ ፡ ተቀባይም ፡ ጽሕፈት ፡ ወይም ፡ በአዛዡ ፡ ጽሕፈት ፡ ነው ። በአንዲት ፡ አጻጻፍ ፡ አንዲት ፡ የምትሆን ፡ ትእዛዝ ፡ በተጻፈች ፡ ጊዜ ፡ ምስክሮች ፡ ባሉበት ፡ ይሁን ። በውስጡዋ ፡ የተሰበሰቡት ፡ (የተጻፉት) ፡ ምስክሮች፡ ይሁኑ ። ቢቻል ፡ ቍጥራቸው ፡ ሰባት ፡ ወይም ፡ አምስት ፡ ይሁን ። ባይቻል ፡ ግን ፡ ፫ ፡ ወይም ፡ ፪ ፡ ይሁን ።

፩ሺ.፪፻፺፪ አዛዡም ፡ የሚጽፍ ፡ ክሆነ ፡ አኳኋኗንና ፡ የቀኑን ፡ ምልክት ፡ የወራሾቹንም ፡ ስም ፡ በእጁ ጽሕፈት ፡ ይጻፍ ። እነሆ ፡ እገሌንና ፡ እገሌን ፡ የእኔ ፡ ወራሾች ፡ አደረግኋቸው ፡ ይበል ። የማይ ጽፍ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ምስክር ፡ የሚሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ስለእርሱ ፡ ፈንታ ፡ የወራሾቹን ፡ ስም ፡ ይጻፉ ። የጻፉትና ፡ በውስጧ ፡ የተጠቀሰው ፡ አዛዥ ፡ ምስክር ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ። ለሚያዝዙ ለት ፡ ሰው ፡ ግን ፡ አይገባውም ። ዳግመኛም ፡ በውስጧ ፡ የወራሾች ፡ አጻጻፋቸው ፡ በውስጧ ፡ በተጻፈው ፡ ተስማምተናል ፡ ብለው ፡ ይሁን ።

፩ሺ.፪፻፺፫ ያለጽሕፈት ፡ የምትሆን ፡ ግን ፡ ጽሑፍን ፡ በመተናኮል ፡ አይሁን ። ያለጽሕፈት ፡ የምትሆንስ ፡ ስለጽሕፈት ፡ ሥራ ፡ ትሆናለችና ፡ ያለ ምስክር ፡ አይገባም ። ያለ ፡ ምስክሮችም ፡ መኖር ፡ አይቻልም ። መክ ፡ ፲፩ ። ትእዛዝ ፡ በታዘዘለት ፡ ሰው ፡ ጽሑፍ ፡ ሊሆን ፡ አይገባም ።

፩ሺ.፪፻፺፬ መክ ፡ ፺፬ ፡ ፲፯ ። ጠስ ፡ ፺፪ ። አዛዥ ፡ ከተዋት ፡ ገንዘብ ፡ አስቀድሞ ፡ የሚያሻው ፡ ለመግነዙ ፡ ለመቃብር ፡ ቆፋሪዎች ፡ ለመቃብሩ ፡ ያሰበትን ፡ ዕዳ ፡ ወይም ፡ ግብር ፡ ለመክፈል ፡ ሊያወጣጡ ፡ ይገባል ። ከእርሷ ፡ በቀር ፡ ባይኖርበት ።

፩ሺ.፪፻፺፭ ጠስ ፡ ፴፯ ። በታዘዘበት ፡ ገንዘብ ፡ ውስጥ ፡ ከዘጠኝ ፡ ቀኖች ፡ አስቀድሞ ፡ ሊፈላለጉ ፡ አይገባም ። ትእዛዝስ ፡ እርሷን ፡ ካልሠራ ፡ በሚገባ ፡ ቃል ፡ ትሻራለች ። በመሥራትም ፡ ቢሆን፡ ይኸውም ፡ እንደመሸጥ ፡ ከባርነት ፡ ነፃ ፡ እንደ ማውጣት ፡ ሴት ፡ ባሪያ ፡ እንደማግባት ፡ ያለ ፡

ፋደስ ፡ ለእመ ፡ ዘረወ ፡ ዘአማኅፀንዎ ፡ ኪያሁ ፡ አው ፡ ለእመ ፡ አስተዋፅአ ፡ ኪያሁ ፡ አሰተዋፅ አተ ፡ ዘያወፅአ ፡ እምልከናሁ ፣ አው ፡ አስተዋ ፅአተ ፡ ዘያበጥል ፡ ሰሞ ፡ ወዕዋቄሁ ። ወከመ ፡ ኢይትወከፍ ፡ ዘተእዘዘት ፡ ሎቱ ፡ በሕይወቱ ፡ ለዘአዘዘ ፡ ኪያሃ ፡ ወከሊኦቱ ፡ ለዘነሥአ ፡ ኪያሃ፡ እምድኅረ ፡ ዕረፍቱ ፡ ወበተኃጥኦቱ ፡ ለዘተአ ዘዘ ፡ ሎቱ ፡ እምቅድመ ፡ ተኃጥኦቱ ፡ ለዘአዘዘ ።

፩ሺ፪፻፵፮ ጠሰ ፡ ፹ወ፩ዱ ፡ ወትፀራዕ ፡ በትእዛዝ ፡ እንተ ትመጽእ ፡ እምድኅሬሃ ፡ እመኒ ፡ ኮነት ፡ እንተ ፡ ቀደመት ፡ በጽሒፍ ።

፩ሺ፪፻፵፯ መክ ፡ ፹ወ፯ቱ ፡ ኢይትፌጸም ፡ ንዋየ ፡ አዛዚ ፡ ለእመ ፡ ሀሎ ፡ ንዋየ ፡ ባዕድ ፡ ዘአንበለ ፡ ለእመ ፡ ኢወሀብዎ ፡ ለበዓለ ፡ ንዋይ ።

፩ሺ፪፻፵፰ ጠሰ ፡ ፴ወ፫ቱ ፡ መክ ፡ ፲ወ፫ቱ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘአዙዝ ፡ ሎቱ ፡ እምቅድመ ፡ ውእቱ ፡ ይትመጠው ፡ ዘእዙዝ ፡ ሎቱ ፡ ዘኢኮነ ፡ ምእ መነ ፡ በጊዜ ፡ ትእዛዝ ፡ አው ፡ እምድኅሬሁ ፡ አው ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ናሁ ፡ ሠርዐ ፡ ላዕለ ፡ ሕይ ወተ ፡ አዛዚ ፡ በሕምዝ ፡ አው ፡ በካልእ ።

፩ሺ፪፻፵፱ ጠሰ ፡ ፹ወ፫ቱ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ትእዛዘ ፡ ዚአሁ ፡ እምተዋርሶ ፡ ዘይትመለክ ፡ ወወራሲስ ፡ ዘይደልዎ ፡ ካልእ ፡ ወለእመ ፡ ኢይከውን ፡ ዘተ ጽሕፈ ፡ በዘቀደመ ፡ ውስተ ፡ መጽሐፍ ፡ ወሰ ማዕታት ፡ ውስቴቱ ፡ ወዘአንበለ ፡ ዝንቱ ፡ ለእመ ፡ ኢነገረ ፡ በአንተ ፡ ዘአዘዝዎ ፡ ሎቱ ፡ ወበዘእማኅፀንዎ ፡ ቦቱ ።

፩ሺ፪፻፶ ዳግምኒ ፡ በእንተ ፡ ዘይኤዝዝ ፡ ወኢይቀውም ፡ ትእዛዙ ፡ ለዘኢኮነ ፡ ብጹሐ ፡ አምጣን ፡ ወዘ ኢኮነ ፡ ግዑዘ ፡ ወዘኢኮነ ፡ ለባዌ ፡ ወኅሩየ ፡ ዘይ በቍዕ ፡ ለትእዛዝ ፡ በከመ ፡ ተጽሕፈ ፡ በአን ቀጸ ፡ ሐፃኒ ፡ ወይደልዎ ፡ ለአዛዚ ፡ ለእመ ፡ ኢኮነ ፡ ዘይኤዝዙ ፡ ሎቱ ፡ ጠቢበ ፡ ወማእምረ ፡ ከመ ፡ ይሚም ፡ ላዕሌሁ ፡ ዘየዐቅቦ ፡ ወይዝክር ፡ ኪያሁ ፡ ውስተ ፡ መጽሐፈ ፡ ትእዛዝ ። ገላትያ ፡ ፬ቱ ፡ ወወራሲስ ፡ እምጣነ ፡ ሕፃን ፡ ውእቱ ፡ አልቦ ፡ ፍልጠት ፡ ማእከሌሁ ፡ ወማእከለ ፡ አግ ብርት ፡ ወእንዘ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአሙ ፡ ለኵ ሎሙ ፡ ወባሕቱ ፡ ይትዐቀብ ፡ ታሕተ ፡ እደ ፡ ሐፃኒ ፡ ወመጋቢ ፡ እስከ ፡ ይበጽሕ ፡ ዕድሜ ፡ ዘዐደሞ ፡ አቡሁ ።



ነው ። ይልቁንም ፡ አደራ ፡ ያስጠበቁትን ፡ ገን ዘብ ፡ ቢበትን ፡ ወይም ፡ ከባለቤትነት ፡ የሚያ ወጣውን ፡ ማወጣጣት ፡ ወይም ፡ ስሙንና ፡ መታወቂያውን ፡ የሚያጠፋ ፡ ማወጣጣት ፡ ቢያ ወጣጣ ፡ እርሷን ፡ ያዘዘ ፡ ሰው ፡ በሕይወቱ ፡ እርሷን ፡ የተቀበለም ፡ ሰው ፡ ከዕረፍቱ ፡ በኋላ ፡ በመክልከሉ ፡ ያዘዘ ፡ ሰው ፡ ከመታጣቱ ፡ አስቀ ድሞ ፡ የታዘዘለት ፡ በመታጣቱ ፡ የታዘዘችለትን እንዳይቀበል ፡ ነው ።

፩ሺ፪፻፵፮ ጠስ ፡ ፹፩ ። ምንም ፡ በጽሑፍ ፡ የቀደመች ፡ ብትሆን ፡ በኋላዋ ፡ በምትመጣ ፡ ትእዛዝ ፡ ትፈ ርሳለች ።

፩ሺ፪፻፵፯ መክ ፡ ፹፯ ፡ ለባለገንዘቡ ፡ ካልሰጡት ፡ በቀር የባዕድ ፡ ገንዘብ ፡ ካለ ፡ የአዛዥ ፡ ገንዘብ ፡ አይ ፈጸምም ።

፩ሺ፪፻፵፰ ጠስ ፡ ፴፫ ። መክ ፡ ፲፫ ። የታዘዘለት ፡ ሰው ፡ ያዘዙለትን ፡ ከመቀበሉ ፡ አስቀድሞ ፡ በትእዛዝ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ በኋላ ፡ አማኝ ፡ ያልሆነ ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ በአዛዥ ፡ ሕይወት ፡ ላይ ፡ በመርዝ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ እነሆ ፡ ክፉ ፡ የሠራ ፡ ቢሆን ፡ አይፈጸምም ።

፩ሺ፪፻፵፱ ጠስ ፡ ፹፫ ። ትእዛዙ ፡ ከውርስ ፡ ገንዘብ ፡ ቢሆን ፡ የሚገባውም ፡ ወራሽ ፡ ሌላ ፡ ቢሆን ። በደብዳቤውም ፡ ውስጥ ፡ በቀደመው ፡ የተጻፈ ፡ ካልሆነ ፡ ምስክሮቹም ፡ በውስጡ ፡ ከሌሉ ፡ ከዚህ ፡ በቀር ፡ ስለአዘዙለት ፡ አደራም ፡ ስለአስ ጠበቁት ፡ ባይናገር ።

፩ሺ፪፻፶ ሁለተኛውም ፡ ስለ ፡ አዛዚ ፡ ይናገራል ። አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ነፃ ፡ የወጣ ፡ ካልሆነ ፡ ራሱን ፡ ያልቻለ ፡ በአንቀጸ ፡ ሐፃኒ ፡ እንደተጻፈ፡ ለትእዛዝ ፡ የሚጠቅም ፡ አስተዋይ ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ያልሆነ ፡ ትእዛዙ ፡ አይጸናም ። የሚያዙ ለት ፡ ሰው ፡ ብልህ ፡ ዐዋቂ ፡ ካልሆነ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ የሚጠብቀው ፡ ሊሾምለት ፡ ይገባዋል ። እርሱንም ፡ በትእዛዙ ፡ ደብዳቤ ፡ ያስተውል ። ገላትያ ፡ ፬ ። ወራሽም ፡ ሕፃን ፡ በነበረበት ፡ ወራት ፡ ለሁሉም ፡ ጌታ ፡ ሲሆን ፡ በእርሱና ፡ በባሮቹ ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ የለውም ። አባቱ ፡ የቀጠረው ፡ ቀን ፡ እስኪደርስ ፡ ድረስ ፡ ገንዘቡ ፡ በሐፃኒና ፡ በመጋቢ ፡ እጅ ፡ ይጠበቃል ፡ እንጂ ፡

አንቀጽ ፡ ፵፩ ።

፩ሺ፪፻፺፩ ጠስ ፡ ፳ወ፩ዱ ፡ ወለእመ ፡ እዘዘ ፡ ዘሀሎ ፡ ታሕተ ፡ ምግብና ፡ አው ፡ ዘኢኮነ ፡ ብጹሐ ፡ አምጣን ፡ አው ፡ ገብር ፡ አው ፡ ሕጹጸ ፡ አእምሮ ፡ ወኅጡአ ፡ ልቡና ፡ ኢይቀውም ፡ ትእዛዘሙ ፡ ወለእመ ፡ ሞተ ፡ ሐፃኒ ፡ ሶበ ፡ ኮነ ፡ ዘእንበለ ፡ ሐፃኒ ፡ ወካልኡኒ ፡ ወውእቱ ፡ እንዘ ፡ ግዑዝ ፡ ወካልእ ፡ እንዘ ፡ ውእቱ ፡ ለባዊ ፡ ወሰዉር ፡ ዘተወልደ ፡ እንዘ ፡ ዕዉሩ ፡ አው ፡ ተጻደቀ ፡ ሎቱ ፡ ለዝንቱ ፡ ትደሉ ፡ ትእዛዙ ።

፩ሺ፪፻፺፪ መጅ ፡ ፳ወ፪ቱ ፡ ወዘሂ ፡ ተወልደ ፡ እንዘ ፡ ውእቱ ፡ በሃም ፡ አው ፡ ጽሙም ፡ እልቦቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ወለጽሙምሰ ፡ ወለበሃም ፡ ዘግብተ ፡ ተጻደቆሙ ፡ ዝንቱ ፡ እመ ፡ ይትከሀሎሙ ፡ ጽሒፍ ፡ ይቀውም ፡ ትእዛዞሙ ፡ ወለዐብድሰ ፡ ኢይቀውም ፡ ትእዛዙ ። ወዓዲ ፡ ለነብርኒ ፡ ኢይደልዎ ፡ ዘእንበለ ፡ በትእዛዘ ፡ ዘይመልክ ።

፩ሺ፪፻፺፫ ጠስ ፡ ፳ወ፩ዱ ፡ ወዘሂ ፡ ኮነ ፡ ብጹሐ ፡ እምጣን ፡ ለገቢረ ፡ ጽሒፍ ፡ ወፈቀደ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ማእከለ ፡ ደቂቁ ፡ ትእዛዘ ፡ በጽሒፍ ፡ ለያእምሮሙ ፡ ለእለ ፡ ያወርሶሙ ። ወለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ይኅድግ ፡ ለብእሲቱ ፡ አው ፡ ለሰብእ ፡ አፍአ ፡ መጽሐፈ ፡ ትእዛዝ ፡ አው ፡ ዘግዕዛን ፡ ያእምሮሙ ፡ ለወራሲያኒሁ ፡ በሀልዎቶሙ ፡ ለእለ ፡ ሰምዐ ፡ ይከውኑ ፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ ሰምዐ ፡ ሳዕለ ፡ ፈጽሞተ ፡ ዝንቱ ።

፩ሺ፪፻፺፬ ወእምከመ ፡ ፈቀደ ፡ ከመ ፡ ይወልጥ ፡ ምክሮ ፡ ወይትመየጥ ፡ እምኔሁ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይሥጥጦ ፡ ለውእቱ ፡ መጽሐፍ ፡ ወየሐድስ ፡ ካልእተ ፡ ትእዛዘ ፡ ዘያጤይቅ ፡ ባቲ ፡ ምክረ ፡ ዚእሁ ፡ ዘደኅረ ፡ ወከይሃ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ በሀልዎተ ፡ ፪ቱ ፡ አው ፡ ፭ቱ ፡ ሰማዕት ። ወይዝክር ፡ ሎሙ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ናሁ ፡ ገብረ ፡ ዘንተ ፡ ምክረ ፡ ባሕቱ ፡ ውእቱ ፡ ኢይፈቅድ ፡ ከመ ፡ ይፈጽም ፡ አላ ፡ ይፈቅድ ፡ ገቢረ ፡ ካልእ ፡ ወእምዝ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ትእዛዘ ፡ ፍጹመ ።

፩ሺ፪፻፺፭ ጠስ ፡ ፳ወ፭ቱ ፡ ወእመሰ ፡ ኀደገ ፡ ንዋየ ፡ ወጸሐፎ ፡ እምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ለካልእ ፡ ወኢዘከረ ፡ አዕርዮተ ፡ ለቀዳማዊ ፡ ለይትካፈልዎ ፡ ኵሎሙ ፡ ለንዋይ ።

፩ሺ፪፻፺፮ ጠስ ፡ ፳ወ፮ቱ ፡ ወዘይኤዝዝ ፡ እምድኅረ ፡ ገቢረ ፡ ትእዛዝ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይወስክ ፡ ዲቤሃ ፡ ወከመ ፡ ያንትግ ፡ እምኔሃ ፡ ጽሒፎ ፡ በሀልዎተ ፡ ሰማዕት ፡ በዘይከውኑ ፡ ሰምዐ ።

በገንዘቡ ፡ ስለሚያዝዝ ።

፩ሺ፪፻፺፩ ጠስ ፡ ፳፩ ። በመተዳደር ፡ ስር ፡ ያለ ፡ ወይም ፡ እካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰ ፡ ወይም ፡ ባሪያ ፡ ወይም ፡ እውቀት ፡ የጐደለውና ፡ አእምሮውን ፡ ያጣ ፡ ቢያዝዝ ፡ ትእዛዛቸው ፡ አይጸናም ። ሞግዚት ፡ ቢሞት ፡ ያለሞግዚትም ፡ ቢሆን ። ሁለተኛውም ፡ ነፃ ፡ ሳለ ፡ ሌላውም ፡ እስተዋይ ፡ ሲሆን ፡ ዕዉር ፡ ሁኖ ፡ የተወለደ ፡ ዕዉር ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ ድንገት ፡ ያገኘው ፡ ትእዛዙ ፡ ትገባለች ፡ (ትፀናለች) ።

፩ሺ፪፻፺፪ መጅ ፡ ፳፪ ። ዲዳ ፡ ወይም ፡ ደንቆሮ ፡ ሁኖ ፡ የተወለደም ፡ ትእዛዝ ፡ የለውም ። ዲዳና ፡ ደንቆሮ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ደዌ ፡ ድንገት ፡ ያገኛቸው ፡ ቢሆኑ ፡ መጻፍ ፡ ከተቻላቸው ፡ ትእዛዛቸው ፡ ይጸናል ። ለዕብድ ፡ ግን ፡ ትእዛዙ ፡ አይጸናም ። ዳግመኛም ፡ ለባሪያ ፡ በገዥው ፡ ትእዛዝ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አይገባውም ።

፩ሺ፪፻፺፫ ጠስ ፡ ፳፩ ። ጽሑፍ ፡ ለማድረግ ፡ እካለ ፡ መጠን ፡ ያደረሰ ፡ ቢሆን ፡ በልጆቹ ፡ መካከል ፡ ትእዛዙን ፡ በጽሕፈት ፡ ሊያደርገው ፡ ቢወድ ፡ ለሚያወርሳቸው ፡ ያስታውቃቸው ። ለምሽቱ ፡ ወይም ፡ ለውጭ ፡ ሰው ፡ የትእዛዝ ፡ ወይም ፡ የነፃነት ፡ ደብዳቤ ፡ ሊተው ፡ ቢወድ ፡ ይህን ፡ ለመፈጸም ፡ ምስክር ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ምስክር ፡ የሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ባሉበት ፡ ለወራሾቹ ፡ ያስታውቃቸው ።

፩ሺ፪፻፺፬ ምክሩን ፡ ሊለውጥ ፡ ከእርሱም ፡ ሊመለስ ፡ ቢወድ ፡ ያንን ፡ ጽሑፍ ፡ ቀዶ ፡ የኋለኛውን ፡ ምክሩን ፡ የሚያስረዳበት ፡ ሁለተኛዋን ፡ ትእዛዝ ፡ ሊያደርስ ፡ እርሷንም ፡ ሰባት ፡ ወይም ፡ አምስት ፡ ምስክሮች ፡ ባሉበት ፡ ሊያደርግ ፡ ይገባዋል ። እነሆ ፡ ይህንን ፡ ምክር ፡ እርሱ ፡ እንዳደረገ ፡ ያስታውሳቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ ሊፈጽም ፡ አይወድም ። ሌላ ፡ ሊያደርገው ፡ ይወዳል ፡ እንጂ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፍጹም ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲያደርግ ፡ ነው ።

፩ሺ፪፻፺፭ ጠስ ፡ ፳፭ ። ገንዘቡን ፡ ቢተው ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ለሌላው ፡ ቢጽፈው ፡ ለመጀመሪያው ፡ መሻሩን ፡ ካልጠቀሰ ፡ ገንዘቡን ፡ ሁሉም ፡ ይከፈሉት ።

፩ሺ፪፻፺፮ ጠስ ፡ ፳፮ ። የሚያዝዝም ፡ ትእዛዝ ፡ ከማድረግ ፡ በኋላ ፡ በሚመሰክሩ ፡ ገንዘብ ፡ ምስክሮች ፡ ባሉበት ፡ ጽፎ ፡ በእርሷ ፡ ላይ ፡ ሊጨምር ፡ ወይም ፡ ከእርሷ ፡ ሊቀንስ ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ.፪፻፶፯ ጽወ፩ዱ ፡ ወእመሰ ፡ ኢፈቀደ ፡ ዘይኤዝዝ ፡ ከመ ፡ ያእምሮሙ ፡ ለእለ ፡ ይከውኑ ፡ ስምዐ ፡ በጽሕፈተ ፡ ዘእሁ ፡ ይጠብልሎ ፡ ለመጽሐፍ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜሁ ፡ ወሬጺሞ ፡ የሀበሙ ፡ ለእለ ፡ ይከውኑ ፡ ስምዐ ፡ ወይብሎሙ ፡ ዛቲ ፡ ትእዛዝ ፡ መጽሐፍ ፡ ትእዛዝ ፡ ዘእየ ፡ ይእቲ ፡ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ስምዐ ፡ ይኩኑ ፡ ለማዕተት ፡ በ፩ዱ ጊዜ ፡ ወይኅትምዎ ።

፩ሺ.፪፻፶፰ ወለእመ ፡ ተከሥተ ፡ ከመ ፡ አዛዚ ፡ ኮነ ፡ ያፈቅድ ፡ ከመ ፡ ይገብር ፡ ካልአነ ፡ ሰብአ ፡ ወኢፈጸመ ፡ ቃሎ ፡ ኢይረስ ፡ ወኢ ፡ እለ ፡ ዘከርሙ ፡ ውእቱ ። ወለእመ ፡ ሀለዎሙ ፡ ለእኁዊሁ ፡ ንዋይ ፡ ዘተደመረ ፡ ኢይክልእዎ ፡ ለአ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ከመ ፡ የእኅዝ ፡ በክፍሉ ፡ ዘእሁ ።

፩ሺ.፪፻፶፱ ትሕ ፡ ዘ፲ወ፪ቱ ፡ ወለእመ ፡ ዐለዋሁ ፡ ለብእሲ ፡ ፪ቲ ፡ አንስት ፡ ወእፍቀራ ፡ ለአሐቲ ፡ እምኔሆን ፡ ወጸልአ ፡ ለካልእታ ፡ ወወለደ ፡ እምኔሆን ፡ ውሉደ ፡ ወፈቀደ ፡ በጊዜ ፡ ሞቱ ፡ ከመ ፡ ያውርሶሙ ፡ ንዋየ ፡ ዘእሁ ፡ ለደቂቅ ፡ ኢይደልዎ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ያዐቢ ፡ ወልዳ ፡ ለእንተ ፡ አፍቀራ ፡ እምወልዳ ፡ ለእንተ ፡ ጸልአ ።

፩ሺ.፪፻፷ ግልስ ፡ ለዘይኤዝዝ ፡ ሎቱ ፡ መክ ፡ ፫ቱ ፡ ኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ እምእለ ፡ ተግህዱ ፡ በወጻእ ፡ እምትእዛዝ ፡ እምላክውያት ፡ ወእምሃይማኖት ፡ ወዘይመልክ ፡ ካልአ ፡ እንበለ ፡ እምላክ ፡ ወእምግባሩ ፡ ዘተመትረ ፡ እምሥርዓተ ፡ ምእመናን ፡ ከመ ፡ ይደመር ፡ ምስለ ፡ ኃጥአን ፡ እስመ ፡ ሐዋርያ ፡ ይቤ ፡ አይ ፡ ሱታፌ ፡ ቦሙ ፡ ለምእመናን ፡ ምስለ ፡ እለ ፡ ኢየአምኑ ፡ ወእዘዘሙ ፡ ለምእመናን ፡ ከመ ፡ ይትፈለጡ ፡ እምእሉ ፡ ወዘይመስልዎሙ ፡ እስመ ፡ ሬሰ ፡ እምእሚን ፡ ኀበ ፡ ክሕደት ፡ ውኅበ ፡ ካልአን ፡ እከይት ፡ ዘውእቶሙ ፡ ዘምዎ ፡ ወዘይመስልዎሙ ፡ ለእሉ ። ለእመ ፡ ኢተፈልጡ ፡ ወኢነስሐ ፡ ወኢተመይጡ ፡ መንገለ ፡ እሚን ፡ ከመ ፡ ይትካፈሉ ፡ ንዋየ ፡ ተዋርሶ ፡ ወእምድኅረ ፡ ተፈልጦሰ ፡ እምኔሃ ፡ ኢኮነ ፡ በከመ ፡ ተነግረ ፡ በእንቀጸ ፡ ርስት ፡ ወይቀውም ፡ ትእዛዝ ፡ ለወራስያን ፡ ኵሎሙ ፡ እው ፡ ለመንፈቆሙ ፡ እው ፡ ለካልእ ፡ እምኔሆሙ ፡ በዘከነ ፡ እፍእ ፡ እምዘይደልዎሙ ፡ ተዋርሶ ።



፩ሺ.፪፻፶፯ ፳፩ ። አዛዥ ፡ ምስክሮች ፡ የሚሆኑትን ፡ በጽሕፈቱ ፡ ሊያስታውቃቸው ፡ ባይወድ ፡ የኑዛዜውን ፡ ጽሑፍ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ይብዳቤውን ፡ ያሽገው ። ከጨረሰም ፡ በኋላ ፡ ምስክር ፡ ለሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ይህች ፡ የደብዳቤ ፡ ትእዛዝ ፡ የኔ ፡ ትእዛዝ ፡ ናት ፡ ብሎ ፡ ይስጣቸው ። ከዚህ ፡ በኋላም ፡ ምስክሮች ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ይመስክሩ ። ይፈርሙበትም ።

፩ሺ.፪፻፶፰ አዛዥ ፡ ሊሎችን ፡ ሰዎች ፡ ሊጠቅስ ፡ የሚወድ ፡ እንደሆነ ፡ ቢታወቅ ፡ ቃሉንም ፡ ባይፈጽም ፡ አይወረስ ። እራሱ ፡ ያስታወሳቸውም ፡ ሰዎች ፡ በወንድሞቹም ፡ የተጨመረ ፡ ገንዘብ ፡ ቢኖራቸው ፡ ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ በድርሻው ፡ እንዲያገኝ ፡ አይከለከሉት ።

፩ሺ.፪፻፶፱ ትሕ ፡ ፲፪ ። ለአንድ ፡ ሰው ፡ ሁለት ፡ ሚስቶች ፡ ቢኖሩት ፡ ከእነርሱ ፡ አንዲቱን ፡ ቢወድ ፡ ሌላይቱንም ፡ ቢጠላ ፡ ከእነርሱም ፡ ልጆችን ፡ ቢወልድ ፡ በሚሞትበትም ፡ ጊዜ ፡ ገንዘቡን ፡ ለልጆቹ ፡ ሊያወርሳቸው ፡ ቢወድ ፡ ከሚወዳት ፡ ሚስቱ ፡ የወለደውን ፡ ልጅ ፡ ከሚጠላት ፡ ሚስቱ ፡ ከወለደው ፡ ልጅ ፡ ሊያበልጥ ፡ አይገባውም (ዘዳ ፡ ፳፩ ፡ ፲፭ - ፲፯) ።

፩ሺ.፪፻፷ ሦስተኛው ፡ ስለሚያዙለት ፡ ሰው ፡ ይናገራል ። መክ ፡ ፫ ። ከእምላክ ፡ ትእዛዛትና ፡ ከሃይማኖት ፡ በመውጣት ፡ ከታወቁት ፡ ወገን ፡ ሊሆን ፡ አይገባም ። ከእምላክ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ጣዖት ፡ የሚያመልክ ፡ ወይም ፡ ምግባሩ ፡ ከኃጥአን ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ከምእመናን ፡ ጎዳና ፡ የተለየ ፡ ሊሆን ፡ አይገባም ። ሐዋርያ ፡ ለምእመናን ፡ ካላመኑ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ምን ፡ አንድነት ፡ አላቸው ፡ ብሏልና ። ከሃይማኖት ፡ ወደ ፡ ክህደት ፡ ወደሌሎቹም ፡ ክፋቶች ፡ ስለ ሄዱ ፡ እኒኽውም ፡ ዝሙትና ፡ እኒህንም ፡ የሚመስሏቸው ፡ ናቸው ። (፪ ፡ ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፲፬ -፲፮) ። ተለይተው ፡ ካልተመ ፡ ወደሃይማኖትም ፡ ካልተመለሱ ፡ የውርሱን ፡ ገንዘብ ፡ ሊካፈሉ ፡ አይገባቸውም ። ከእርሷ ፡ ከተለዩ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ በአንቀጸ ፡ ርስት ፡ እንደተነገረው ፡ አይደለም ። ለወራሾቹ ፡ ሁሉ ፡ ወይም ፡ ለእኩሌቶቹ ፡ ወይም ፡ ውርስ ፡ ከሚገባቸው ፡ በውጭ ፡ በሆነው ፡ ከእነርሱ ፡ ሌሎችም ፡ ቢሆን ፡ ትእዛዝ ፡ ይጸናል ።

አንቀጽ ፡ ፵፩ ።

፩ሺ.፪፻፷፩ መከ ፡ ፪ቱ ፡ ወዘሂ ፡ ተጽሕፈ ፡ ሎቱ ፡ በውስተ ፡ ትእዛዝ ፡ በንዋየ ፡ ተዋርሶ ፡ ለእመ ፡ ተዳደቃ ፡ ለእንተ ፡ ተጽሕፈት ፡ ወተነሥአት ፡ ግብተ ፡ እኮ ፡ ዘይደሉ ፡ ከመ ፡ ይትከላእ ፡ እምኔሃ ። ወለእመ ፡ ኢተዳደቃ ፡ ወኢመጽአ ፡ ላዕሌሃ ፡ መጻኢ ፡ ወእምዝ ፡ ፈቀደ ፡ ከመ ፡ የሀብ ፡ ክፍለ ፡ ዚአሁ ፡ ለካልኡ ፡ ወከመ ፡ ኢይንሣእ ፡ ምንተኒ ፡ እምርስቱ ፡ ወዝኒ ፡ ብዉሕ ፡ ሎቱ ።

፩ሺ.፪፻፷፪ ጠስ ፡ ፴ ፡ ወይደሉ ፡ ከመ ፡ ይጽሐፍ ፡ ሙቁሕ ፡ ዘሂ ፡ ተሰደ ፡ ለወራሲ ፡ እንዘ ፡ ይሴፎ ፡ ግብአተ ፡ ዚአሁ ፡ ወለእመ ፡ ተዳደቀ ፡ ለወራሲ ፡ ተሞቅሖ ፡ አው ፡ ስደት ፡ እምድኅረ ፡ አዘዘ ፡ ጽሒፎ ፡ ይደልዎ ፡ ሎቱ ፡ ነሢአ ፡ ዘአዘዘ ፡ ሎቱ ፡ እምድኅረ ፡ ድኅነቱ ፡ ወእመኒ ፡ በግብአቱ ።

፩ሺ.፪፻፷፫ ጠስ ፡ ወለእመ ፡ ቦ ፡ ለአሐዱ ፡ ወልድ ፡ ዘነገደ ፡ ወበጽሐ ፡ ኅቤሁ ፡ ዜና ፡ ሞቱ ። ወአዘዘ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ንዋዩ ፡ ለካልኡ ፡ በምክንያተ ፡ ንግደቱ ፡ ወልዱ ፡ እንዘ ፡ ሕያው ፡ ውእቱ ይኩን ፡ ርስቱ ፡ ለወልዱ ፡ ሀየንተ ፡ ውእቱ ፡ ዘተአዘዘ ፡ ሎቱ ።

፩ሺ.፪፻፷፬ ክፍል ፡ ወይደሉ ፡ ከመ ፡ የአዝዙ ፡ ለፅንስት ፡ ለባሕቲታ ፡ እንበለ ፡ ዘትፀውሮ ፡ በከርሣ ፡ ወለዘፀንሰቶሂ ፡ በባሕቲቱ ፡ እንበሌሃ ፡ ወባሕቱ ፡ ኢይጸንዕ ፡ ሎቱ ፡ ምንትኒ ፡ ለእመ ፡ ኢወፅአ ፡ ሕያወ ፡ አው ፡ ለእመ ፡ ኢተወልደ ፡ በዕድሜ ፡ ፅንስ ፡ እምጊዜ ፡ ተጽሕፈ ፡ ወተአዘዘ ፡ ሎቱ ። ወለእመ ፡ ተአዘዘ ፡ ለፅንስት ፡ ወለዘተፀንሰ ፡ በከርሣ ፡ በምንትኒ ፡ ወወለደት ፡ መንታ ፡ ይክፍሉ ፡ ማእከለ ፡ ፪ሆሙ ፡ ዕሩየ ። ወለእመ ፡ ተወልደ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ሕያወ ፡ ወካልኡኒ ምዉተ ፡ ይኩን ፡ ኵለንታሁ ፡ ለሕያው ። ወለእመ ፡ አርአየ ፡ ዝከረ ፡ ወፈለጠ ፩ደ ፡ ተባዕተ ፡ አልቦ ፡ ዘይወርስ ፡ ዘእንበሌሁ ፡ ወይከውን ፡ አማነ ፡ ጽሒፈ ፡ ትእዛዝ ፡ ለገብር ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ግዑዘ ፡ በጊዜ ፡ ዘይደልዎ ፡ ይኩን ፡ ንዋዩ ፡ ሎቱ ፡ ወእመ ፡ አኮሰ ፡ ዘእግዚኡ ፡ ውእቱ ።

፩ሺ.፪፻፷፭ ራብዕ ፡ በእንተ ፡ ዘይኤዝዙ ፡ ኪያሁ ፡ ኢይጸንዕ ፡ ቃሉ ፡ ለእመ ፡ ኢኮነ ፡ ምልክናሁ ፡ ለዘይኤዝዝ ፡ ወምጣኔሁሰ ፡ ኀበ ፡ ፪ቱ ፡ ፍናዋት ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ራብዕተ ፡ እዴሃ ፡ ለዘይወርስዋ ፡ ወካልእ ፡ ሣልስተ ፡ ራብዕተ ፡ እዴሃ ፡ ለኀ

በገንዘቡ ፡ ስለሚያዝዝ ።

፩ሺ.፪፻፷፩ መከ ፡ ፯ ። በውርሱ ፡ ገንዘብ ፡ በትእዛዝ ፡ የተጻፈለት ፡ ሰው ፡ የተጻፈችውን ፡ ድንገት ፡ ጥፋት ፡ ቢያገኛት ፡ በድንገትም ፡ ብትወሰድ ፡ ከእርሷ ፡ ሊከለከል ፡ የሚገባ ፡ አይደለም ። ድንገት ፡ ጥፋት ፡ ባያጋጥማት ፡ ክፉ ፡ አድራጊ ፡ ባይመጣባት ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ድርሻውን ፡ ለሌላው ፡ ሊሰጥ ፡ ከርስቱም ፡ ምንምን ፡ ላይወስድ ፡ ቢወድ ፡ ይህም ፡ ለእርሱ ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ.፪፻፷፪ ጠስ ፡ ፴ ። የታሠረ ፡ የተሰደደም ፡ መመለሱን ፡ ተስፋ ፡ እያደረገ ፡ ለወራሹ ፡ ሊጽፍ ፡ ይገባል ። ወራሹን ፡ ጽፎ ፡ ካዘዘለት ፡ በኋላ ፡ እሥራት ፡ ወይም ፡ ስደት ፡ ድንገት ፡ ቢያገኘው ፡ ከዳነ ፡ በኋላ ፡ የሚመለስም ፡ ቢሆን ፡ ያዘዙለትን ፡ መውሰድ ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ.፪፻፷፫ ጠስ ፡ ለአንድ ፡ ሰው ፡ ወደሩቅ ፡ አገር ፡ የሄደ ፡ ልጅ ፡ ቢኖረው ፡ የሞቱም ፡ ወሬ ፡ ቢደርሰው ፡ በሕይወት ፡ ሳለ ፡ ልጁ ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡ በመሄዱ ፡ ምክንያት ፡ ገንዘቡ ፡ ለሌላ ፡ እንዲሆን ፡ ቢያዝዝ ፡ ስለታዘዘለት ፡ ሰው ፡ ፈንታ ፡ ርስቱ ፡ ለልጁ ፡ ይሁን ።

፩ሺ.፪፻፷፬ ክፍል ፡ ለጸነሰች ፡ ሴት ፡ በሆዱ ፡ የተሸከመችውን ፡ ፅንስ ፡ ለይቶ ፡ ለብቻዋ ፡ ከእርሷም ፡ ለይቶ ፡ ለፀነሰችው ፡ ብቻ ፡ ሊያዝዝ ፡ ይገባል ። ነገር ፡ ግን ፡ ሕያው ፡ ሆኖ ፡ ካልተወለደ ፡ ወይም ፡ ከተጻፈለትና ፡ ከታዘዘለት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ በጽንሱ ፡ ጊዜ ፡ ልክ ፡ ካልተወለደ ፡ ምንም ፡ አይጸናለትም ። ለፀነሰች ፡ ሴት ፤ ወይም ፡ በሆዷ ፡ ለተፀነሰው ፡ በማናቸውም ፡ ቢታዘዝ ፡ መንታ ፡ ብትወልድ ፡ በሁለቱ ፡ መካከል ፡ በትክክል ፡ ይከፈሉ ። ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ ሕያው ፡ አንዱ ፡ ምዉት ፡ ሁኖ ፡ ቢወለድ ፡ ሁሉም ፡ ለሕያው ፡ ይሁን ። ለይቶ ፡ አንዱን ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ በማስታወስ ፡ ቢገልጽ ፡ ከርሱ ፡ በቀር ፡ የሚወርስ ፡ የለም ። ለባሪያ ፡ ትእዛዝ ፡ መጻፍ ፡ የታመነ ፡ ይሆናል ። በሚገባው ፡ ጊዜም ፡ ነፃ ፡ የወጣ ፡ ቢሆን ፡ ገንዘቡ ፡ ለእርሱ ፡ ይሁን ። ያም ፡ ባይሆን ፡ ግን ፡ የጌታው ፡ ነው ።

፩ሺ.፪፻፷፭ ዐራተኛው ፡ እርሱን ፡ ስለሚያዙት ፡ ይናገራል ፡ ለአዛዥ ፡ ገንዘቡ ፡ ካልሆነ ፡ ቃሉ ፡ አይጸናም ። አስተያየቱም ፡ ሁለት ፡ መንገድ ፡ አለው ። ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ ዐራተኛዋ ፡ እጅ ፡ ለሚወርሳት ፡ ነው ። ሁለተኛው ፡ ካራት ፡ እጅ ፡ ሢሶውን ፡

ዲግ ፡ ወካልእኒ ፡ ትሥልስት ፡ ወራብዓይስ ፡ ውእቱ ፡ ድልው ፡ ወውእቱ ፡ ዘድልው ። ቀዳ ሚሰ ፡ ፍና ፡ እኂዘ ፡ ቀኖና ፡ ዘተነግረ ፡ በእንቲ እሁ ።

፩ሺ፪፻፷፮ መከ ፡ ፩ዱ ፡ ወዘሂ ፡ ጸሐፈ ፡ ትእዛዘ ፡ ለይረስ ፡ ውሉዱ ፡ በከመ ፡ ፈቀደ ፡ ወየ ሀብ ፡ ለእዋልዲሁ ፡ ለለአሐቲ ፡ መክፈልተ ፡ ሕዜሆን ፡ ወይክፍል ፡ ንዋዮ ፡ ኀበ ፡ ፬ቱ ። ወለ እመ ፡ ፈቀደ ፡ ከመ ፡ ይመጽውት ፡ በምንትኒ ፡ እምንዋዩ ፡ ይመጽውት ፡ ራብዕተ ፡ እዴሁ ፡ ወእ ምዝ ፡ ያቅም ፡ ለእዋልዲሁ ፡ ራብዕተ ፡ እድ ፡ ለሕዜሆን ፡ ወይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ በት ሥልስት ፡ እም ፡ ፬ቱ ፡ ዘፈቀደ ፡ ወይረስ ፡ ወልዱ ፡ በከመ ፡ ፈቀደ ፡ እስመ ፡ ሕግነ ፡ ትኤ ዝዝ ፡ ሎቱ ፡ ወከመ ፡ ይኩኑ ፡ ውሉዱ ፡ ለብእሲ፡ ዘይወርሱ ፡ ፫ተ ፡ እም፬ቱ ፡ ንዋዩ ። ወለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ከመ ፡ ይወስከ ፡ ለእዋልዲሁ ፡ ምንተኒ፡ ንዋየ ፡ ዝንቱለ ፡ ብዉሕ ፡ ሎቱ ፡ ወእመሰ ፡ አል ቦቱ ፡ ውሉድ ፡ ያውርስ ፡ ንዋዮ ፡ ለዘፈቀደ ።

፩ሺ፪፻፷፮ መከ ፡ ፩ ። ትእዛዝ ፡ ያጻፈ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡ ልጆቹ ፡ ይውረሱ ። ለሴቶች ፡ ልጆቹ ፡ ለእያንዳንዲቱ ፡ የመታጫቸውን ፡ ድርሻ ፡ ይስጥ ፡ ገንዘቡንም ፡ ካራት ፡ ይክፈል ፡ ከገን ዘቡ ፡ በምንም ፡ ሊመጸውት ፡ ቢወድ ፡ አራ ተኛውን ፡ እጅ ፡ ይመጽውት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አራተኛዋን ፡ እጅ ፡ ለሴቶቹ ፡ ልጆች ፡ ለማ ጫቻቸው ፡ ይወስን ። ካራቱ ፡ በሲሶው ፡ የወደ ደውን ፡ ሊያደርግ ፡ ይገባዋል ። ወንድ ፡ ልጁ ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡ ይውረስ ። ሕጋችን ፡ ታዛለችና ፡ ልጆቹ ፡ ከገንዘቡ ፡ ካራቱ ፡ እጅ ፡ ሦስቱን ፡ እጅ የሚወርሱ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ለሴቶች ፡ ልጆቹ ፡ ምንም ፡ ገንዘብ ፡ ሊጨምር ፡ ቢወድ ፡ ይህ ፡ ለእርሱ ፡ ይገባዋል ። ልጆች ፡ ባይኖሩት ፡ ግን ፡ ገንዘቡን ፡ ለወደደው ፡ ያውርስ ።

፩ሺ፪፻፷፯ ወናሁ ፡ ተነግሩ ፡ በዝንቱ ፡ ቀኖና ፡ ፪ቱ ፡ ምክራት ፡ ወብሂሎቱ ፡ ዘውስቴቱ ፡ ኢይኩን ፡ ዘእንበለ ፡ ይትከሠት ፡ ወዝንቱ ፡ ቀኖና ፡ ኢኮነ፡ ድልወ ፡ ለ፩ዱ ፡ ዘእንበለ ፡ በምክረ ፡ ፪ቱ ፡ ወፍ ካሬሁሰ ፡ ኢኮነ ፡ ክሡተ ፡ በዝንቱ ፡ ኢይበዝኅ ፡ ቀኖና ፡ ፩ዱ ፡ እምነ ፡ ካልኡ ። ወምክርሰ ፡ ዳግ ማዊ ፡ በእሕጽጾ ፡ ቀናኖት ፡ እለ ፡ ነገሩ ፡ በእን ቲእሁ ።

፩ሺ፪፻፷፯ እነሆ ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ሁለት ፡ አስተያየ ቶች ፡ ተነግረዋል ። በውስጡ ፡ የተነገረው ፡ ሳይገለጽ ፡ አይሁን ። ይህ ፡ ሥርዓት ፡ በሁለተ ኛው ፡ አስተያየት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ላንዱ ፡ የተገባ ፡ አይደለም ። ትርጓሜውም ፡ በዚህ ፡ የተገለጸ ፡ አይደለም ። ያንዱ ፡ ሥርዓት ፡ ከሁ ለተኛው ፡ አይበዛም ። ሁለተኛው ፡ አስተያየት፡ ግን ፡ ስለእርሱ ፡ የሚናገሩትን ፡ ሥርዓቶች ፡ በማላነስ ፡ ነው ።

፩ሺ፪፻፷፰ መከ ፡ ፲ቱ ፡ ይደልዎ ፡ ለብእሲ ፡ ከመ ፡ ይክ ፍል ፡ ኀበ ፡ ፫ቱ ፡ ወራብዓየሰ ፡ ንዋዮ ፡ ይግ በር ፡ ለዘእፍቀረ ፡ ወያትርፍ ፡ ፩ደ ፡ ራብዓየ ፡ ለወራሲሁ ፡ ዘእንበለ ፡ ተወስኮ ። ዘ፲ወ፰ቱ ፡ ወውእቱ ፡ ሥሉጥ ፡ ላዕለ ፡ ፫ቱ ፡ ወራብዓየሰ ፡ ንዋዮ ፡ የሀብ ፡ ለዘፈቀደ ፡ ወይክፍል ፡ እምው ቱሂ ፡ ለውሉዱ ፡ ተእዛዝያን ።

፩ሺ፪፻፷፰ መከ ፡ ፲ ። ለሰው ፡ ገንዘቡን ፡ ከሦስት ፡ ሊከፍል ፡ ይገባዋል ። ከገንዘቡ ፡ አራተኛውን ፡ ግን ፡ ለወደደው ፡ ያድርግ ። አንዱን ፡ አራተኛ ውንም ፡ ያለ ፡ ጭማሪ ፡ ለወራሹ ፡ ያስቀር ። ፲፰፡ እርሱ ፡ በ፫ቱ ፡ እጅ ፡ ሥልጣን ፡ አለው ። ከገ ንዘቡ ፡ አራተኛውን ፡ ግን ፡ ለወደደው ፡ ይስጥ ። ከዚኽውም ፡ ለሚታዘዙ ፡ ልጆች ፡ ይከ ፈል ።

፩ሺ፪፻፷፱ ዘ፺ወ፰ቱ ፡ ወለአመ ፡ ጸሐፈ ፡ ብእሲ ፡ ትእ ዛዘ ፡ ወሠርዐ ፡ በንዋዩ ፡ ምንተኒ ፡ ኢተፈጸመ ፡ ትርብዕት ፡ ወሐጸ ፡ መንፈቅ ፡ ወትርብዕት ፡ ዐቅሞት ፡ ወፈጽሞት ፡ ቦቱ ፡ ርስተ ፡ ወውእቱ ትርብዕት ፡ ለሰብእ ፡ ነኪራን ፡ ይርእዩ ፡ በዝ ንቱ ፡ ለእመ ፡ ይከውን ፡ ጋእዝ ፡ ለወራሳያኒሁ ፡

፩ሺ፪፻፷፱ ፺፰ ። ሰው ፡ ትእዛዝ ፡ ቢጽፍ ፡ በገንዘቡ ፡ ምንምን ፡ ቢወስን ፡ እርቦ ፡ አልተፈጸመም ። እኩሌታውም ፡ ጐደለ ። እርቦም ፡ መወሰንና ፡ መፈጸም ፡ በርስቱ ፡ አለበት ። ይኸውም ፡ እርቦ፡ ለሌሎቹ ፡ ሰዎች ፡ ነው ። በዚህ ፡ ይፍረዱ ። ለወራሾቹ ፡ ከገንዘቡ ፡ እርቦ ፡ የተነሣ ፡ ክርክር፡

እምትርብዕተ ፡ ንዋዩ ፡ ይኩን ፡ ዘእቀመ ። ወለ
እመሰ ፡ አ.ቆመ ፡ ራብዕተ ፡ እዴሁ ፡ ይሁብር ፡
መንፈቀ ፡ ምስለ ፡ ራብዕተ ፡ እድ ፡ ዘቆመ ፡ ወይ
ፈጽም ፡ ቦቱ ፡ ከዊነ ፡ ተዋርሶ ፡ ዘውእቱ ፡ ራብ
ዕተ ፡ እድ ።

፩ሺ፱፻፸ ሥርዋጽ ፡ ሐተታ ፡ ቦኑ ፡ ይደልዎ ፡ ለብእሲ ፡
ከመ ፡ ያውርስ ፡ ኵሎ ፡ ርስተ ፡ ዚአሁ ፡ ለብእ
ሲቱ ፡ እንዘ ፡ አልቦ ፡ እምኔሁ ፡ ውሉድ ፡ ወቦኑ ፡
ለእመ ፡ ቦቱ ፡ ፪ቱ ፡ ውሉድ ፡ ወኵሉ.ቀን ፡ በው
ስተ ፡ መጽሐፈ ፡ ትእዛዙ ፡ ይኅድግኑ ፡ ሳተ ፡
ምንተኒ ፡ እው ፡ ያቅም ፡ላቲ ፡ እምድኅረ ፡ ወሀባ ፡
ሕዝያ ። ይቤ ፡ ይደልዎ ፡ እንከ ፡ ለብእሲ ፡ ከመ ፡
ይጽሐፍ ፡ ትእዛዞ ፡ ወይረሲ ፡ በውስቴታ ፡ ስመ ፡
ወራስያን ፡ ዘፈቀደ ፡ ወባሕቱ ፡ ዘንቤሰ ፡ ከመ ፡
ዳግማዊ ፡ ድልው ፡ በበይነ ፡ ኀጸት ፡ ፷ቱ ።

፩ሺ፱፻፸፩ ቀዳማዊ ፡ እስመ ፡ ክልኤሆሙ ፡ ቃላት ፡ ተነ
ግሩ ፡ በውስተ ፡ ፩ዱ ፡ መጽሐፍ ፡ እም፩ዱ ፡
ምክር ፡ ወተጠንቀቀ ፡ ዳግማዊ ፡ በብዙኅ ፡ ቀዋ
ናት ፡ በጥንተ ፡ መጽሐፉ ፡ ወውስተ ፡ ማእከሉ ፡
ወበተፍጻሜቱ ፡ ቀዳማዊ ፡ ተነግረ ፡ በውስተ ፡
ቀኖና ፡ ወበምክረ ፡ በዓለ ፡ መጽሐፍ ፡ ወይትዐ
ወቅ ፡ እምተሰናሰዎተ ፡ ቃላቲሁ ፡ እለ ፡ ይጠ
ነቀቁ ፡ በውስተ ፡ መካናት ፡ ፍሉጣት ።

፩ሺ፱፻፸፪ ወባሕ ፡ ዳግማዊ ፡ ነገር ፡ ዘተነግረ ፡ በውስተ ፡
ምክር ፡ ቀዳማዊ ፡ ኢኮነ ፡ ከሡተ ፡ ፍካሬሁ ፡
እስመ ፡ እምኔሁ ፡ ይትከሠቱ ፡ ፪ቱ ፡ ምክራት ፡
ወቃልሰ ፡ ዘተነግረ ፡ በውስተ ፡ ዳግማዊ ፡ ኢተ
ከሥተ ፡ እምኔሁ ፡ ዘእንበለ ፡ ዳእሙ ፡ ምክር ፡
ዳግማዊ ፡ ወእኂዞቱ ፡ ለዘይትሌለይ ፡ ይደሉ ።

፩ሺ፱፻፸፫ ወባሕ ፡ ግልስ ፡ ምክርስ ፡ ቀዳማዊ ፡ ይትነ
ገር ፡ በውስተ ፡ ጥንተ ፡ መጽሐፍ ፡ ወምክርኒ ፡
ዳግማዊ ፡ ተነግረ ፡ እምድኅሬሁ ፡ በጥንተ ፡
መጽሐፍ ፡ ወበማእከሉ ፡ ወበፍጻሜሁ ፡ ወደ
ኃራዊ ፡ ይነሥቶ ፡ ለቀዳማዊ ።

፩ሺ፱፻፸፬ ራብዕ ፡ ናሁ ፡ ተነግረ ፡ በዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡
ከመ ፡ ብዉሕ ፡ ለብእሲ ፡ ይግበር ፡ በንዋዩ ፡
ዘፈቀደ ፡ ወብዉሕ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡
እመኒ ፡ በመንፈቀ ፡ ወእመኒ ፡ በራብዕተ ፡
እዴሁ ፡ ወይረሲ ፡ በዘፈቀደ ፡ ዘእንበለ ፡ ተከ
ልአ ፡



ቢሆን ፡ የወሰነው ፡ ይሁን ። እራተኛው ፡ እጅ ፡
ካልጸና ፡ ከአራተኛው ፡ እጅ ፡ ጋር ፡ የጸናው ፡
እኩሌታው ፡ ይሻራል ። የእወራረስንም ፡ ሁኔታ
በእርሱ ፡ ይፈጽም ። ይኸውም ፡ እራት ፡ እጅ ፡
ነው ።

፩ሺ፱፻፸ ሥርዋጽ ። ሐተታ ፡ ለሰው ፡ ከእርሱ ፡ ልጆች ፡
ሳይኖሯት ፡ ርስቱን ፡ ሁሉ ፡ ለሚስቱ ፡ ሊያወር
ሳት ፡ በእውኑ ፡ ይገባዋልን ። በትእዛዙ ፡ ደብ
ዳቤ ፡ ውስጥ ፡ የተቈጠሩ ፡ ሁለት ፡ ልጆች ፡ ቢኖ
ሯት ፡ ምንም ፡ ምን ፡ ሊተውላት ፡ ወይም ፡ማጫ
ዋን ፡ ከሰጣት ፡ በኋላ ፡ ሊወስንባት ፡ ይገባልን ?
እንግዲህ ፡ ለሰው ፡ ትእዛዙን ፡ ይጽፍ ፡ ዘንድ ፡
በውስጥም ፡ የወደዳቸውን ፡ የወራሾቹን ፡
ስም ፡ ሊያደርግ ፡ ይገባዋል ፡ አለ ። ነገር ፡ ግን ፡
እንደ ፡ ሁለተኛው ፡ የተገባ ፡ ነው ፡ ያልነው ፡
ስለ ፡ ፰ ፡ ነገሮች ፡ ነው ።

፩ሺ፱፻፸፩ እንደኛ ፡ ሁለቱም ፡ ቃሳት ፡ ካንድ ፡ እስተ
ያየት ፡ በአንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ተነግረዋልና ።
ሁለተኛውም ፡ በብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ በመጽሐፉ
መጀመሪያ ፡ በመካከሉም ፡ በመጨረሻውም ፡
ተጽፏል ። መጀመሪያው ፡ በእንደኛው ፡ መጽ
ሐፍና ፡ በባለ ፡ መጽሐፉ ፡ እስተያየት ፡ ተነ
ገረ ። በተለዩ ፡ ቦታዎች ፡ ከተጻፉ ፡ ከቃላቱ ፡
መስማማት ፡ የተነሳ ፡ ይታወቃል ።

፩ሺ፱፻፸፪ ሁለተኛው ፡ እስተያየት ፡ በመጀመሪያው ፡
እስተያየት ፡ የተነገረው ፡ ነገር ፡ ትርጓሜው ፡
የተገለጸ ፡ አልሆነም ። ከእርሱ ፡ ሁለት ፡ እስተ
ያየቶች ፡ ይገለጻሉና ። በሁለተኛው ፡ የተነገ
ረው ፡ ቃል ፡ ከእርሱ ፡ አልተገለጸም ። በሁ
ለተኛው ፡ እስተያየት ፡ ነው ፡ እንጂ ። የሚረዳ
ውን ፡ መያዝ ፡ ይገባል ።

፩ሺ፱፻፸፫ ፫ተኛው ፡ እስተያየት ፡ በመጀመሪያው ፡
በመጽሐፉ ፡ መጀመሪያ ፡ ይነገራል ። ሁለተ
ኛውም ፡ እስተያየት ፡ ከእርሱ ፡ ቀጥሎ ፡ በመ
ጽሐፉ ፡ መጀመሪያ ፡ በመካከሉም ፡ በመጨ
ረሻውም ፡ ተነገረ ። የኋለኛውም ፡ የፊተኛውን፡
ይሽረዋል ።

፩ሺ፱፻፸፬ ፀራተኛው ፡ ሰው ፡ በገንዘቡ ፡ የወደደውን ፡
ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ እንዲገባው ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ፡
ተነገረ ። ያደርግም ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣን ፡ አለው ።
በእኩሌታውም ፡ ቢሆን ፡ በአራተኛውም ፡
እጅ ፡ ቢሆን ፡ ያለመከልከል ፡ በወደደው ፡
ያድርግ ።

፩ሺ፪፻፸፭ ኃምስ ፡ ናሁ ፡ አቅደምን ፡ ነጊረ ፡ ከመ ፡ ለት እዛዝ ፡ እንተ ፡ ተጽሕፈት ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይግበርዋ ፡ በእንተ ፡ ዘይቤ ፡ እግዚእብሔር ፡ ወበ እንተ ፡ ግብሮሙ ፡ ለለባውያን ፡ እስመ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ አዘዞሙ ፡ ለደቂቅከ ፡ ፈጺመ ፡ ብሂለ ፡ ወኢሞቅሐ ፡ ቃሎ ፡ ኢ ፡ በንስቲት ፡ ወኢ ፡ በብዙኅ ፡ ወለባውያንሂ ፡ ሶበ ፡ አዘዙ ፡ አስተባውሖ ፡ ቃል ፡ ኢሞቅሑ ፡ ዘእንበለ ፡ በዘ ይሜኒ ፡ በጊዜ ፡ ጽሒፈ ፡ ትእዛዝ ። ወበቍዔትስ ፡ እንተ ፡ ሀለወት ፡ ውስተ ፡ ዳግማዊ ፡ ይፈ ይፍድ ፡ በከመ ፡ ተጠየቀ ።

፩ሺ፪፻፸፮ ሳድስ ፡ ልቡና ፡ ይፈትሕ ፡ ከመ ፡ ብዉሕ ፡ ለለባዊ ፡ ይግበር ፡ በንዋዩ ፡ በከመ ፡ ይፈቅድ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ሥሉጥ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወአልቦ ፡ ዘይከልአ ፡ እምነ ፡ ሠይጦቱ ፡ ወኢ ፡ እምአቅሞቱ ፡ አው ፡ ከመ ፡ ይመጽውት ፡ አው ፡ የሀብ ፡ ለዘፈቀደ ፡ ወዝንቱ ፡ ብውሕ ፡ ሎቱ ፡ መንፈቁ ፡ ወትርብዕቱ ፡ አዶሁ ።

፩ሺ፪፻፸፯ ሳብዕ ፡ በቀኑዔትሰ ፡ ትትፌጸም ፡ በምክር ፡ ዳግማዊ ፡ ፈድፋደ ፡ እምቀዳማዊ ፡ እስመ ፡ ዘይእኅዞ ፡ ለምክር ፡ ዳግማዊ ፡ ይትከሀሎ ፡ ለእመ ፡ ርእየ ፡ በቀኑዔተ ፡ ውስተ ፡ ምክር ፡ ቀዳማዊ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ኪያሁ ፡ በፍትሐ ፡ ዚአሁ ፡ ወከመ ፡ የአኅዞ ፡ ለምክር ፡ ቀዳማዊ ። ወሶበ ፡ ርእየ ፡ ከመ ፡ ሀለወ ፡ በቀኑዔት ፡ ውስተ ፡ ምክር ፡ ዳግማዊ ፡ ኢይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ከማሁ ፡ ለቀዳማዊ ።

፩ሺ፪፻፸፰ ሳምን ፡ አሕስሞስ ፡ ይመጽእ ፡ ፈድፋደ ፡ በምክር ፡ ቀዳማዊ ፡ ወምክርሰ ፡ ዳግማዊ፡ ካልእ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ መንፈቀ ፡ ደቂቁ ፡ ለዘይኤዝዝ ፡ ጽሒፎ ፡ ብዑላን ፡ ወመንፈቆሙ ፡ ነዳያን ፡ ወይደሉ ፡ ሎሙ ፡ ከመ ፡ የአዝዝ ፡ ዘይፈደፍድ ፡ ለነዳያን ። ወዳዲ፡ ይደሉ ፡ ይኩኑ ፡ ወራስያኒሁ ፡ አብዕልተ ፡ ወይትከሀሎ ፡ ከመ ፡ ያቅም ፡ ወይመጽውት ፡ ወየግዕዞሙ ፡ ለብዙኃን ።

፩ሺ፪፻፸፱ ወፍጻሜሁስ ፡ ለዘተብህለ ፡ ውስተ ፡ ጸናኔ ፡ ይሊዎቱ ፡ ለቀዳማዊ ፡ እስመ ፡ ዘያወርስ ፡ ናሁ ፡ ይጸላእ ፡ በነበ ፡ ወራስያኒሁ ፡ በግፍዕ ፡ አው ፡ በቅንእት ፡ አው ፡ ከመ ፡ ዘያፈቅር ፡ ካልአኒሆሙ ። ወይደሉ ፡ በምክር ፡ ዳግማዊ ፡ ከመ ፡ ይትከላእ ፡ እምዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ ፈድፋደ ፡ እስመ፡



፩ሺ፪፻፸፭ አምስተኛ ፡ እነሆ ፡ የተጻፈችውን ፡ ትእዛዝ ፡ ሊያደርጓት ፡ እንደሚገባ ፡ አስቀድመን ፡ ተናገርን ። እግዚአብሔር ፡ ስላዘዘ ፡ ስለአስተዋዮችም ፡ ሥራ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጆችህን ፡ እዘዛቸው ፡ በማለት ፡ ፈጽሚልና ። (፪ ፡ ነገ ፡ ፳ ፡ ፩) ። በጥቂትም ፡ ቢሆን ፡ በብዙም ፡ ቢሆን ፡ ቃሉን ፡ አልወሰነም ፡ አስተዋዮችም ፡ በቃል ፡ ማሰናበትን ፡ ባዘዙ ፡ ጊዜ ፡ ትእዛዝን ፡ በመጽሐፍ ፡ በሚገባ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አልወሰኑም ። በሁለተኛው ፡ ያላቸው ፡ ጥቅስም ፡ እንደተነገረው ፡ ይበዛል ።

፩ሺ፪፻፸፮ ስድስተኛ ፡ ሳስተዋይ ፡ ሰው ፡ በገንዘቡ ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡ ሊያደርግ ፡ እንደሚገባው ፡ ልቡና ፡ ይፈርዳል ። በእርሱ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ አለውና ። ከመሸጡ ፡ ወይም ፡ ከመንከለቱ ፡ ወይም ፡ ይመጸውት ፡ ዘንድ ፡ ወይም ፡ ለወደደው ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ የሚከለክለው ፡ የለም ። ይህ ፡ እኩሌታው ፡ አራተኛውም ፡ እጅ ፡ ለእርሱ ይገባዋል ።

፩ሺ፪፻፸፯ ሰባተኛ ። ጥቅስ ፡ ከፊተኛው ፡ ይልቅ ፡ በሁለተኛው ፡ አስተያየት ፡ ትፈጸማለች ። ሁለተኛውን ፡ አስተያየት ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ በፊተኛው ፡ አስተያየት ፡ ጥቅም ፡ ካየ ፡ በእርሱ ፡ ፍርድ ፡ እርሱን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ የቀደመውንም ፡ አስተያየት ፡ ሊይዝ ፡ ይቻለዋልና ። በሁለተኛው ፡ አሳተያየት ፡ ጥቅም ፡ እንዳለ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ እንደ፡ ፊተኛው ፡ እንዲሁ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ አይገባውም ።

፩ሺ፪፻፸፰ ስምተኛ ። ማሳዘንስ ፡ በፊተኛው ፡ አስተያየት ፡ ፈጽሞ ፡ ይመጣል ። ሁለተኛው ፡ አስተያየትስ ፡ ሌላ ፡ ነው ። ይህ ፡ ጽፎ ፡ ለሚያዝዝ ፡ ሰው ፡ ከልጆቹ ፡ እኩሌቶቹ ፡ ባለጸጎች ፡ እኩሌቶችም ፡ ድሆች ፡ ሊሆኑ ፡ ይገባልና ። የሚበልጠውን ፡ ለነዳያን ፡ ያዝዝላቸው ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ። ዳግመኛም ፡ ወራሾቹ ፡ ባለጸጎች ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ይገባል ። ሊጐልትና ፡ ምጽዋት ፡ ሊመጸውት ፡ ብዙዎችንም ፡ ነፃ ፡ ሊያወጣቸው ፡ ይቻለዋል ።

፩ሺ፪፻፸፱ ወደ ፡ ማዘንበል ፡ የተባለውን ፡ መፈጸምስ ፡ ለፊተኛው ፡ አግባቡ ፡ ነው ። እነሆ ፡ አውራሽ ፡ በወራሾቹ ፡ ዘንድ ፡ በግፍ ፡ ወይም ፡ በቅንነት ፡ ወይም ፡ ሌሎቻቸውን ፡ እንደሚወድ ፡ ይጠላልና ። በሁለተኛው ፡ አስተያየት ፡ ከዚህ ፡ ሁሉ፡ ፈጽሞ ፡ ሊርቅ ፡ ይገባል ። ላውራሽ ፡ በሚገባ ፡

ለእውራሲ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ በዘይ
ደሉ ፡ እመኒ ፡ ከመ ፡ የሀቦሙ ፡ በእዴሁ ፡ ዘፈ
ቀደ ፡ እው ፡ ከመ ፡ ይሢጥ ፡ ሎሙ ፡ አው ፡ ከመ
ይእመን ፡ ከመ ፡ በሙ ፡ በላዕሌሁ ፡ እምነ ፡ ዕዳ፡
ዘፈቀደ ፡ እው ፡ ከመ ፡ ይሢጥ ፡ ለካልእኒሁ ፡
አው ፡ ይእመን ፡ በዘይሁብ ፡ ሎሙ ፡ ወእምከ
መሰ ፡ ጸንዐ ፡ በዝንቱ ፡ ሠናይ ። ወመንፈቀ ፡
ለራብዕ ፡ ይደልዎ ፡ ለዘ.የወርሰ ፡ ከመ ፡ ያውር
ሶሙ ፡ ለፈራህያነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወፈድፋ
ደሰ ፡ ከመ ፡ ይፍርሆ ፡ ውእቱ ፡ ለእግዚአብሔር፡
እስመ ፡ ውእቱ ፡ ናሁ ፡ ሀለወ ፡ ይትናጸር ፡
ምስለ ፡ ሞት ።

፩ሺ፪፻፺፰ ወኢያስተዋዕእ ፡ መንፈቀ ፡ ንዋዩ ፡ ወራብ
ዕተ ፡ እዴሁ ፡ ዘእንበለ ፡ ለዘይደልዎሙ ፡
እመኒ ፡ ለደቂቁ ፡ እው ፡ ለውሉደ ፡ ውሉዱ ፡
ወእመኒ ፡ ለእዝማዲሁ ፡ እው ፡ ለእናግድ ፡
እው ፡ ለጽኑስ ፡ እምነ ፡ ጽኑስ ፡ ወለዘይደልዎ ፡
እምነ ፡ ዘኢይደልዎ ። ወይኩን ፡ መጋቤ ፡ ምእ
መነ ፡ ወጠቢበ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ድልወ ፡ ለው
ዳሴ ፡ ወለነሢእ ፡ ዕሤት ፡ እምኀበ ፡ መኰንን ፡
ሰማያዊ ፡ ሎቱ ፡ ሰብሐት ።

፩ሺ፪፻፺፰፩ በደሰ ፡ መፍትው ፡ ለክርስቲያናዊ ፡ ከመ ፡
ኢይዝሩ ፡ ንዋዮ ፡ ኀበ ፡ እልቦቱ ፡ ድኂን ፡ ወለ
ዘሂ ፡ እዘዘ ፡ ቦቱ ፡ ዘይፈደፍድ ፡ እምነ ፡ መን
ፈቀ ፡ ወራብዕተ ፡ እድ ፡ ይፀራዕ ፡ ዘእንበለ ፡
ዘይደልዎሙ ፡ ለወራሲያን ፡ እምድኅረ ፡ ዕረ
ፍቱ ፡ ወዘሂ ፡ ወሀበ ፡ ኪያሁ ፡ በሕይወቱ ፡
እምነ ፡ ግዕዛን ፡ ወእቅሞት ፡ ወምጽዋት ፡ ወው
ሂብ ፡ እመኒ ፡ ኮነ ፡ በጥዒናሁ ፡ እው ፡ በደዌሁ ፡
እንበለ ፡ ይኩን ፡ እንቡዘ ፡ ልብ ፡ ኢይኁልቍዎ
ምስለ ፡ መንፈቅ ፡ ወራብዕተ ፡ እድ ።

፩ሺ፪፻፺፰፪ ጠሰ ፡ ፳ወ፳ቱ ፡ ወለእመ ፡ ቦ ፡ ዘኮነ ፡ ሎቱ ፡
እምድኅረ ፡ ጸሐፈ ፡ መጽሐፈ ፡ ትእዛዝ ፡ ይደ
ልዎ ፡ ርስት ፡ ለዘይደልዎ ፡ ፡ እመኒ ፡ ኮኑ ፡
ውሉድ ፡ ተባዕተ ፡ እው ፡ እንስተ ፡ ወለእመ ፡
ኮነ ፡ እንበለ ፡ ውሉድ ፡ በጠለ ፡ በእፍልሶ ፡ ትእ
ዛዝ ፡ እምውሉድ ። ወእመሰ ፡ ኮኑ ፡ እለ ፡ ይደ
ልዎሙ ፡ ይረሱ ፡ እምእለ ፡ ተረክቡ ፡ ውሉድ ፡
ተባዕት ፡ ወእንስት ። ወለእመ ፡ ኮነት ፡ መጽ
ሐፈ ፡ ትእዛዝ ፡ ለዘኢኮነ ፡ ወልደ ፡ በጠለ ፡
እንከ ፡ እምድኅረ ፡ ሞቱ ፡ ለእዛዚሁ ፡ እምነ ፡
ዘእዘዙ ፡ ሎቱ ፡ ወይደሉ ፡ ለውሉደ ፡ ውሉድ ፡
ወረሶቶሙ ።



ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ይገባዋልና ። የወደደውን ፡
በእጁ ፡ ሊሰጣቸውም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ሊሸጥ
ላቸው ፡ ወይም ፡ ከዕዳ ፡ ወገን ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡
እንዳላቸው ፡ የወደደውን ፡ ሊያምን ፡ ወይም ፡
ለሌሎቹ ፡ ሊሸጥ ፡ ወይም ፡ ለእነርሱ ፡ በሚሰ
ጠው ፡ ሊያምን ፡ ይገባዋልና ። በዚህ ፡ ቢጸናስ ፡
መልካም ፡ ነው ። የሩቡን ፡ እኩሌታ ፡ እግዚአብ
ሔርን ፡ ለሚፈሩ ፡ ሰዎች ፡ ያወርሳቸው ፡ ዘንድ፡
ላውራሽ ፡ ይገባዋል ። ይልቁንም ፡ እርሱ ፡ እግዚ
አብሔር ን ፡ ይፈራው ፡ ዘንድ ። እነሆ ፡ እርሱ ፡
ከሞት ፡ ጋራ ፡ ይተያያልና ።

፩ሺ፪፻፺፰ የገንዘቡን ፡ እኩሌታ ፡ እራተኛውንም ፡ እጅ ፡
ለሚገባቸው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ እያወጣጣ ።
ለልጆቹ ፡ ወይም ፡ ለልጅ ፡ ልጆቹ ፡ ቢሆን ፡ ለዘ
መዶቹም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ለእንግዶች ፡ ወ
ይም ፡ ከችጋረኛ ፡ ይልቅ ፡ ለችጋረኛ ፡ ከማይገ
ባው ፡ ለሚገባው ፡ ምስጋና ፡ ይግባውና ፡ ከሰማ
ያዊ ፡ ዳኛ ፡ ዘንድ ፡ ምስጋናና ፡ ዋጋ ፡ ለማግኘት
ዝግጁ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ የታመነና ፡ ዐዋቂ ፡
መጋቢ ፡ ይሁን ።

፩ሺ፪፻፺፰፩ በደሰ ፡ ለክርስቲያን ፡ ሰው ፡ ድኅነት ፡ በሌለ
በት ፡ ቦታ ፡ ገንዘቡን ፡ እንዳይበትን ፡ ይገባ
ዋል ። ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ለወራሾቹ ፡ ከሚገባቸው፡
በቀር ፡ ከእኩሌታና ፡ ከአራተኛ ፡ እጅ ፡ የሚበ
በልጥ ፡ ላዘዘበት ፡ ይቀራል ። በሕይወቱ ፡ ከነፃ
ነት ፡ ከገልት ፡ ከምጽዋት ፡ ከስጦታ ፡ ወገን ፡
የሰጠውን ፡ በጤናው ፡ ወይም ፡ ልቡን ፡ ያጣ ፡
ሳይሆን ፡ በበሽታው ፡ ቢሆን ፡ ከእኩሌታውና ፡
ከአራተኛው ፡ እጅ ፡ ጋራ ፡ አይቁጠሩት ።

፩ሺ፪፻፺፰፪ ጠሰ ፡ ፳፩ ። የትእዛዝ ፡ ደብዳቤ ፡ ከጻፈ ፡
በኋላ ፡ ልጅ ፡ የሆነለት ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ርስት ፡
ለሚገባው ፡ ይገባዋል ። ልጆች ፡ ወንዶች ፡
ወይም ፡ ሴቶች ፡ ቢሆኑ ፡ ያለ ፡ ልጅም ፡ ቢሆን፡
ከልጆች ፡ ትእዛዝን ፡ በማዛወር ፡ ይቀራል ።
የሚገባቸውስ ፡ ከሆኑ ፡ ከተገኙት ፡ ከወንዶችና፡
ከሴቶች ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ ይውረሱ ። ትእዛዝ ፡
ላልወለደው ፡ ልጅ ፡ ብትሆን ፡ ከእዛዥ ፡ ሞት ፡
በኋላ ፡ ካዘዙለት ፡ ሰው ፡ እንግዲህ ፡ ቀረ ።
ለልጅ ፡ ልጆች ፡ መውረስ ፡ ይገባቸዋል ።

አንቀጽ ፡ ፵፩ ።

፩ሺ፪፻፹፫ ወእመ ፡ ኮኑ ፡ እለ ፡ ድልዋን ፡ ለርስት ፡ ዘተረክቡ ፡ እምአዝማደ ፡ ዚአሁ ፡ ወኮነት ፡ ይእቲ ፡ ትእዛዝ ፡ ለነኪራን ፡ ይንሥኡ ፡ አዝማደ ፡ ዚአሁ ፡ መንፈቆ ። ወለእመኒ ፡ ኮኑ ፡ አዝማዲሁ ፡ ይክፍሉ ፡ ማእከለ ፡ ዘእዘዙ ፡ ሎቱ ፡ እምነ ፡ ሰብኡ ፡ ወማእከለ ፡ እለ ፡ ተሐደሱ ፡ እምኔሆሙ ፡ በዕሩይ ። ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ፍትሑ ፡ ለዘተአዘዘ ፡ ሎቱ፡ ምስለ ፡ እለ ፡ ሎቱ ፡ ይትሐደሱ ፡ እምድኅረ ፡ መጽሐፈ ፡ ትእዛዝ ።

፩ሺ፪፻፹፬ ዘ፴ወ፩ቱ ፡ ወለእመ ፡ እዘዘ ፡ ለ፩ዱ ፡ መርዔተ ፡ አባግዕ ፡ ይኩኑ ፡ እለ ፡ ተወልዱ ፡ ወለእመ ፡ ሐጹ ፡ ወኮኑ ፡ እስከ ፡ ፩ዱ ፡ አው ፡ ተኃጕሉ ፡ ፍጹመ ፡ ላሰሌሁ ፡ ውእቱ ። ወለእመ ፡ እዘዘ ፡ ለብእሲ ፡ ቤተ ፡ ወውዕየ ፡ በእሳት ፡ ትኩውን ፡ ሎቱ ፡ ምድሩ ።

፩ሺ፪፻፹፭ ወእመኒ ፡ እዘዘ ፡ ለከ ፡ ፩ደ ፡ ገብረ ፡ ምስለ ፡ ረባኑ ፡ ወእምዝ ፡ እምድኅረ ፡ ትእዛዝ ፡ እግዓዞ ፡ አው ፡ ወለጦ ፡ አው ፡ ፈነዎ ፡ በካልእ ፡ ፍና ፡ ግጽ ፡ አው ፡ ሞተ ፡ ይፃእ ፡ እምኀቤከ ፡ ውእቱ ፡ ገብር ፡ ምስለ ፡ ረባኑ ፡ እስመ ፡ ለእመ፡ ኢሀለወ ፡ ሥርው ፡ ኢይሄልዉ ፡ እለ ፡ ተርፉ ፡ ተላውያን ።

፩ሺ፪፻፹፮ ወእመኒ ፡ እዘዘ ፡ በክፍል ፡ እምንዋይ ፡ ምንተኒ ፡ ሣልስተ ፡ እዴ ፡ አው ፡ ራብዕተ ፡ እዴ ፡ ወእምዝ ፡ ተኀጥአ ፡ መንፈቁ ፡ ለውእቱ ፡ ንዋይ ፡ ይኩን ፡ ሎቱ ፡ ንዋይ ፡ ሣልስተ ፡ እዴሁ ለዘተርፈ ፡ አው ፡ ራብዕቱ ።

፩ሺ፪፻፹፯ ወለእመ ፡ እዘዘ ፡ ለመኑሂ ፡ በ፩ዱ ፡ መክፈልት ፡ እምነ ፡ ጸጋሁ ፡ ወእያቀ ፡ ከዋኔሁ ፡ ኢይደልዎ ፡ ለወራሲ ፡ ከመ ፡ ይክልእ ፡ ዘፈለጠ ፡ ሎቱ ። ወእመሰ ፡ ኢፈለጠ ፡ ሎቱ ፡ ወኮነ ፡ እምነ ፡ ብዙኃት ፡ ግብራት ፡ ይኅረይ ፡ ወራሲ ፡ እመቦ ፡ ይሁቦ ፡ መክፈልተ ፡ እምውእቱ ፡ ንዋይ ፡ እንዘ ፡ ኢየኀሪ ፡ እኩየ ፡ አላ ፡ ማእከላየ ፡ አው ፡ የሀቦ ፡ ሎቱ ፡ ሤጠ ፡ ዚአሁ ። ወእመ ፡ ኮነ ፡ ዘኢይትከፈል ፡ የሀቦ ፡ ሎቱ ፡ ሤጦ ፡ እንዘ ኢይትገአዙ ፡ በእንተ ፡ ሤጡ ።

፩ሺ፪፻፹፰ ክፍል ፡ ወትጸንዕ ፡ ትእዛዝ ፡ በእንተ ፡ ንዋይ ለ፩ዱ ፡ ወበእንተ ፡ በቍዔት ፡ ዘገብረ ፡ በርእሱ፡ እመሂ ፡ በፍሬ ፡ አው ፡ በተዓስቦ ፡ አው ፡ በተልእኮ ፡ ለካልእ ፡ በዕድሜ ፡ ዘተሐገገ ፡ መጠነ ፡ ዓመት ፡ እመኒ ፡ ፪ቱ ፡ አው ፡ ፫ቱ ፡ በምጣኔ ፡

በገንዘቡ ፡ ስለሚያዝዝ ።

፩ሺ፪፻፹፫ ከዘመዶቹ ፡ ወገን ፡ የተገኙት ፡ ለርስት ፡ የተዘጋጁ ፡ ቢሆኑ ፡ ይህችም ፡ ትእዛዝ ፡ ለሌሎች ፡ ብትሆን ፡ እኩሌታውን ፡ ዘመዶቹ ፡ ይውሰዱ ። ዘመዶቹም ፡ ቢሆኑ ፡ ከሰዎቹ ፡ ወገን ፡ ባዘዙለትና ፡ ከእነርሱ ፡ ወገን ፡ አዲስ ፡ በሆኑት ፡ መካከል ፡ በትክክል ፡ ይክፈሉ ። ከትእዛዝ ፡ ደብዳቤ ፡ በኋላ ፡ አዲስ ፡ ከሆኑት ፡ (ከተገኙት) ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ የታዘዘለት ፡ ሰው ፡ ፍርድ ፡ ይህ ፡ ነው ።

፩ሺ፪፻፹፬ ፴፩ ። ለአንድ ፡ ሰው ፡ የበግ ፡ መንጋ ፡ ቢያዝዝ ፡ የተወለዱት ፡ ለእርሱ ፡ ይሁኑ ። አንድ ፡ እስኪሆኑ ፡ ድረስ ፡ ቢያንሱ ፡ ጨርሰውም ፡ ቢጠፉ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ነው ። ለሰው ፡ ቤት ፡ ቢያዝዝለት ፡ በእሳትም ፡ ቢቃጠል ፡ ምድሩ ፡ ለእርሱ ፡ ትሆናለች ።

፩ሺ፪፻፹፭ አንድን ፡ ባሪያ ፡ ከልጆቹ ፡ ጋራ ፡ ቢያዝዝልህ ፡ ከትእዛዝ ፡ በኋላም ፡ ነፃ ፡ ቢያወጣው ፡ ወይም ፡ ቢሸጠው ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ዓይነት ፡ መንገድ ፡ ቢልከው ፡ ወይም ፡ ቢሞት ፡ ይህ ፡ ባሪያ ፡ ከልጆቹ ፡ ጋራ ፡ ካንተ ፡ ዘንድ ፡ ይውጣ ። ሥር ፡ ከሌለ ፡ የቀሩት ፡ ተከታዮች ፡ (ጫፎች) ፡ አይኖሩምና ።

፩ሺ፪፻፹፮ ከገንዘቡ ፡ ማናቸውንም ፡ በከፊል ፡ ፫ኛውን፡ እጅ ፡ ወይም ፡ ፬ኛውን ፡ እጅ ፡ ቢያዝዝ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የዚህ ፡ ገንዘብ ፡ እኩሌታው ፡ ቢጠፋ ፡ ከቀረው ፡ ገንዘብ ፡ ፫ኛው ፡ እጅ ፡ ወይም ፡ ዕርቦው ፡ ለእርሱ ፡ ይሁን ።

፩ሺ፪፻፹፯ ለማንም ፡ ከሀብቱ ፡ በ፩ ፡ ድርሻ ፡ ሁኔታዉን ፡ አስታውቆ ፡ ቢያዝዝ ፡ ወራሽ ፡ የለየለትን ፡ ሊከለክለው ፡ አይገባም ። ባይለይለት ፡ ግን ፡ ከብዙ፡ ሥራዎች ፡ ወገን ፡ ቢሆንም ፡ መካከለኛውን ፡ እንጂ ፡ መጥፎዉን ፡ ሳይመርጥ ፡ ከዚህ ፡ ገንዘብ ፡ ድርሻውን ፡ ይስጠው ፡ እንደሆነ ፡ ወይም፡ ዋጋውን ፡ ይሰጠው ፡ ዘንድ ፡ ይምረጥ ። የማይከፈል ፡ ቢሆን ፡ ስለዋጋው ፡ ሳይከራከሩ ፡ ዋጋዉን ፡ ይስጠው ።

፩ሺ፪፻፹፰ ክፍል ። ለአንዱ ፡ ስለገንዘብ ፡ በዓይነቱም ፡ ስላደረገው ፡ ትርፍ ፡ በፍሬዉ ፡ ወይም ፡ በኪራዩ ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ በማገልገል ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ፪ም ፡ ወይም ፡ ፫ ፡ ቢሆን ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ከኪራዩ ፡ በታወቀ ፡ ልክ ፡

ዘተበውቀ ፡ እምነ ፡ ዓስብ ፡ እመኒ ፡ በውሂበ ፍሬ ፡ ዘኢየዐዱ ፡ ኅበ ፡ ካልእ ፡ ፍሬ ፡ አው ፡ ውሂበ ፡ ዓስብ ፡ በዕድሜ ፡ ዘተወሰነ ፡ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ትግባእ ፡ በቍዔተ ፡ ንዋዩ ፡ ለመላኪሃ ፡ ዘእዘዘ ፡ ሎቱ ፡ ኪያሁ ። ወእመኒ ፡ ሞተ ፡ ዘእዘዘ ፡ ሎቱ ፡ በቍዔተ ፡ ዚአሃ ፡ ኢይረስ ፡ ወራሲሁ ፡ ኪያሃ ። ወመላኪሁኒ ፡ ዘተገንቶ ፡ ይምልክ ፡ አግእዞቶ ፡ ወሠይጦቶ ፡ ወመሢጦቶ ፡ ቦቱ ፡ ወእገዞ ፡ ኪያሁ ፡ ዘከመ ፡ ይፈቅድ ፡ እምድኅረ ፡ ተወሰነ ፡ ለከዊን ፡ በቍዔት ፡ ለእግዚእ

፩ሺ.፪፻፹፱ ወዓዲ ፡ ይጸንዕ ፡ ጽሒፈ ፡ ትእዛዝ ፡ በእንተ ፡ እመት ፡ ዘእንበለ ፡ ዕንስ ፡ ዘውስተ ፡ ከርሣ ፡ ወለዕንስኒ ፡ ባሕቲቱ ፡ ዘእንበለ ፡ እመት ። ወለእመ ፡ አዘዘ ፡ ሰዕንስት ፡ ባሕቲታ ፡ ወኢዘከረ ፡ ዕንሳ ፡ ወኢ ፡ እምቅድመ ፡ ትዕንስ ፡ ትከውን ፡ ይእቲ ፡ ምስለ ፡ ዕንሳ ፡ ለዘአዘዘ ፡ ሎቱ ፡ ኪያሃ ፡

፩ሺ.፪፻፺ ኃምስ ፡ በእንተ ፡ ተእዛዚ ፡ ሎቱ ፡ በጽሑፍ ፡ ወቦቱ ፡ ትእዛዛት ፡ ፪ቱ ፡ ተእምኖ ፡ ወምግባት ፡ በዘይመልክ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወሰዘኢያዖቀ ፡ ኪያሁ ፡ አዛዚ ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ በሕይወቱ ፡ ይሥራዕ ፡ ፈታሒ ፡ እምድኅረ ፡ ሞቱ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘእዙዝ ፡ ሎቱ ፡ ኅጡአ ፡ አእምሮ ፡ ይጸንዕ ፡ ጽሒፈ ፡ ትእዛዙ ፡ ላዕለ ፡ ንዋዩ ፡ ፍሉጥ ፡ ዘእንበለ ፡ ካልእ ።

፩ሺ.፪፻፺፩ ወለእመ ፡ አዘዘ ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡ ዘንዋዩ ፡ የእዝዝ ፡ ለክልኤቱ ፡ ኅቡረ ፡ ወኢይፈጽም ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ግብረ ፡ ዚአሁ ፡ ዘእንበለ ፡ ትእዛዘ ፡ ካልኡ ፡ ወከመ ፡ የእዝዝ ፡ ለ፩ዱ ፡ ሀየንተ ፡ ካልኡ ። እመሰ ፡ ተብህለ ፡ እመ ፡ እኮ፡ እገሌ ፡ አው ፡ እገሌ ፡ ወእይኒ ፡ ዘተወከፈ ፡ እምእሉ ፡ አው ፡ እዘዘ ፡ ኪያሃ ፡ ቅድመ ፡ ውእቱኬ ፡ እዛዚ ፡ ዘእንበለ ፡ ካልኡ ። ወእመኒ ፡ ተብህለ ፡ እገሌ ፡ ወእምድኅሬሁ ፡ እገሌ ፡ ኢይደልዎ ፡ ለዳግማዊ ፡ ከመ ፡ ይመጣብ ፡ ባቲ ፡ ዘእንበለ ፡ እምድኅረ ፡ ዐእተ ፡ ቀዳማዊ ፡ እምኔሃ ፡ ወከመ ፡ ኢይትወከፉ ፡ ትእዛዞ ።

፩ሺ.፪፻፺፪ ወእምከመ ፡ መገበ ፡ ዘተእዘዘ ፡ ሎቱ ፡ በምንትኒ ፡ እምትእዛዝ ፡ ዶለወ ፡ ላዕሌሁ ፡ ተወክፎ ፡ ትእዛዝ ፡ ወኢይዓእ ፡ እምዓመተ ፡ ትእዛዝ ፡ ዘእንበለ ፡ በብጽሒቱ ፡ ለዘአዘዘ ፡ ሎቱ ፡ ወተመርሖቱ ። አው ፡ እመ ፡ አበየ ፡ ያብጽሖ ፡ ኀበ ፡ ፈታሒ ፡ ወያስተሥርዕ ፡ ሎቱ ፡ ወይኅድጎ ፡

ወደ ፡ ሁለተኛው ፡ በማይተላለፍ ፡ ፍሬም ፡ ቢሆን ወይም ፡ በተወሰነ ፡ ቀን ፡ ዋጋ ፡ በመስጠትም ፡ ቢሆን ፡ ትእዛዝ ፡ ትጸናለች ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የገንዘቡ ፡ ጥቅም ፡ እርሱን ፡ ላዘዘለት ፡ ለባለቤቷ ፡ ትመለስ ። ጥቅሟን ፡ ያዘዘለት ፡ ሰው ፡ ቢሞትም ፡ ወራሹ ፡ እርሷን ፡ አይውረስ ። የጥንት ፡ ጌታውም ፡ ነፃ ፡ ማውጣቱን ፡ መሸጡን ፡ መመጽወቱን ፡ ለጌታው ፡ ጥቅም ፡ ለመሆን ፡ ከተወሰነ በኋላ ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡ ሊያዝበት ፡ እጅ ፡ ያድርግ ።

፩ሺ፪፻፹፱ ዳግመኛም ፡ በሆዷ ፡ ያለውን ፡ ፅንስ ፡ ለይቶ ፡ ስለ ፡ ባሪያይቱ ፡ ባሪያይቱንም ፡ ለይቶ ፡ ለፅንሱ ፡ ብቻ ፡ ትእዛዝ ፡ መጻፍ ፡ ይጸናል ። ለፀነሰችው ፡ ሴት ፡ ብቻ ፡ ቢያዝዝ ፡ የፀነሰችውንም ፡ ባያነሣ ፡ ከመፅነሷም ፡ አስቀድሞ ፡ ቢሆን ፡ እርሷ ፡ ከፀነሰችው ፡ ጋራ ፡ እርሷን ፡ ላዘዘለት ፡ ሰው ፡ ትሆናለች ።

፩ሺ፪፻፺ አምስተኛ ። በጽሕፈት ፡ ለእርሱ ፡ ስለሚታዘዝ ፡ ይናገራል ። ሁለት ፡ ትእዛዛት ፡ መታመንና በሚያስተዳድርበት ፡ ላይ ፡ መሾም ፡ አሉበት ። አዛዥ ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ ያላሳወቀውን ፡ እርሱ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ዳኛ ፡ ይሥራበት ። የታዘዘለት ፡ ሰው ፡ አእምሮውን ፡ ያጣ ፡ ቢሆን ፡ ከሌላው ፡ በቀር ፡ በተለየ ፡ ገንዘቡ ፡ ላይ ፡ የትእዛዝ ፡ ጽሕፈት ፡ ይጸናል ።

፩ሺ፪፻፺፩ ስለ ፡ ተወዉ ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ ቢያዝዝ ፡ ለሁለቱ ፡ ባንድነት ፡ ይዘዝ ። ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ ያለ ባልንጀራው ፡ ትእዛዝ ፡ ሥራውን ፡ አይፈጽም ። ለአንዱም ፡ ስለሌላው ፡ ፈንታ ፡ ሊያዝዝ ፡ አይገባውም ። ባይሆን ፡ እገሌ ፡ ወይም ፡ እገሌ ፡ ቢባል ፡ ግን ፡ ከእነዚህ ፡ የተቀበለ ፡ ወይም ፡ አስቀድሞ ፡ እርሷን ፡ ያዘዘ ፡ ማንኛውም ፡ ቢሆን ፡ ከባልንጀራው ፡ ተለይቶ ፡ አዛዥ ፡ ነው ። እገሌ ፡ ከእርሱም ፡ በኋላ ፡ እገሌ ፡ ቢባልም ፡ የፊተኛው ፡ ከእርሷ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ሁለተኛው ፡ ሊያስተዳድርባት ፡ ትእዛዙንም ፡ ሊቀበሉት ፡ አይገባውም ።

፩ሺ፪፻፺፪ ከትእዛዝ ፡ በማናቸውም ፡ የታዘ[illegible]ለት ፡ ሰው ፡ ካስተዳደረ ፡ ትእዛዙን ፡ መቀበል ፡ ተገባው ። ያዘዘለት ፡ ሰው ፡ ከመድረሱና ፡ ከመመራቱ ፡ በቀር ፡ ከታዘዘለት ፡ ሹመት ፡ አይውጣ ። ወይም ፡ እንቢ ፡ ቢል ፡ ወደ ፡ ዳኛ ፡ ያድርሰው ። ዳኛውም ፡ እንደዚሁ ፡ ሁኖ ፡ ቢያገኘው ፡ ይቶ

ፈታሒ ፡ ለእመ ፡ ረከበ ፡ ዘከማሁ ፡ አው ፡ ከመ ፡ ይንግሮ ፡ ዘይሥዕሮ ፡ እምዘንዋኒ ፡ ዘተአዘዘ ፡ ቦቱ ፡ ዘከመ ፡ ደዌ ፡ ዘንዋኅ ፡ ሰደሚ ፡ ወመዋቅሔ ፡ ዘንዋኅ ፡ መዋዕል ፡ ወዘከመ ፡ ንግደት ፡ ኀበ ፡ ርኁቅ ፡ አው ፡ ሰደት ፡ ለእመ ፡ እኢሚመ ፡ ዘይሚግብ ፡ እምታሕቴሁ ፡ ምእመን ፡ ወበቋዔ ፡ በግብሩ ፡ አው ፡ ከመ ፡ ይጽናዕ ፡ ላዕሌሁ ፡ እማሬ ፡ ለነሚአ ፡ ትእዛዝ ፡ ዘእሙር ። ወእምድኅረ ፡ አውዕአ ፡ ኢይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይግባእ ፡ ወይኩን ፡ አዛዚ ፡ ወወፂእስ ፡ ዘአቅደመ ፡ ዘክሮቶ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይግባእ ፡ ወይኩን ፡ አዛዚ ፡ በትእዛዘ ፡ ፈታሒ ።

፩ሺ፪፻ ፶፫ ወለዘሂ ፡ ዒጦ ፡ ፈታሒ ፡ ከመ ፡ ይመግብ ፡ ቦቱ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ፍጹመ ፡ ሃይማኖት ፡ ወምእመን ፡ ወበቋዒ ፡ ወእመኒ ፡ ኮነ ፡ እምአዝማዲሁ ፡ ለዘተአዘዘ ፡ ሎቱ ፡ ውእቱ ፡ ዘይደልዎ ፡ ወይግበር ፡ ቦቱ ፡ ለአዝማድ ፡ ምስለ ፡ አዝማድ ፡ እስመ ፡ ዘቅሩብ ፡ ይኩን ፡ ለቅሩብ ።

፩ሺ፪፻ ፶፬ መከ ፡ ፲ወ፮ቱ ፡ ይደልዎ ፡ ለብእሲ ፡ ከመ ፡ ያብእ ፡ ወልዶ ፡ ላዕለ ፡ ጽሒፈ ፡ ትእዛዙ ፡ ዲበ ፡ ንዋዩ ፡ ወይኩን ፡ መጋቢ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ዘንዱገ ።

፩ሺ፪፻ ፶፭ ዘ፲ወ፫ቱ ፡ ወብዉሕ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይሢም ፡ ግብረ ፡ ዚአሁ ፡ ላዕለ ፡ ዘንዱገ ፡ ወይግበር ፡ ኵሎ ፡ ዘይትገበር ፡ ውእቱ ።

፩ሺ፪፻ ፶፮ ዘ፲ወ፬ቱ ፡ ወለእመ ፡ ጸሐፈት ፡ ብእሲት ፡ ትእዛዘ ፡ ለደቂቀ ፡ ወልዳ ፡ ኢብዉሕ ፡ ላቲ ፡ ከመ ፡ ትሢም ፡ ሎሙ ፡ መጋቤ ፡ ወዐቃቤ ፡ እስመ ፡ ይደልዎ ፡ ለአቡሆሙ ፡ በዝንቱ ። ወእመሰ ፡ እልቦሙ ፡ አብ ፡ ይኩን ፡ ሎሙ ፡ መጋቤ ፡ ወዐቃቤ ፡ ወይደሉ ፡ ላቲ ካዕበ ፡ ከመ ፡ ትሢም ሎሙ ፡ መጋቤ ፡ ወዘየዐቅቦሙ ፡ በዘንዱገ ፡ ሎሙ ፡ ባሕቲቱ ።

፩ሺ፪፻ ፶፯ መ፳ ፡ ፲ወ፭ቱ ፡ ወዘሂ ፡ ሞተ ፡ ዘእንበለ ፡ ጽሒፈ ፡ ትእዛዝ ፡ ውንዱገ ፡ ውሉደ ፡ ወተርፉ ፡ ወላድያኒሁ ፡ ወአኃዊሁ ፡ ለይኩን ፡ ትእዛዘ ፡ ርስቱ ፡ ለወላድያኒሁ ፡ ወይመግቡ ፡ ቦቱ ፡ በእምሳለ ፡ መጋቢ ፡ ዘተአዘዘ ፡ ሎቱ ፡ ወእኮ ፡ ለአኃው ፡ ከመ ፡ ይትካፈሉ ፡ ምስለ ፡ ውሉድ ፡ ወኢይደልዎሙ ፡ ከመ ፡ ይትቃወምዎሙ ፡ ለወላድያን ። በዝንቱ ፡ ይትዐወቅ ፡ እሣዚ ፡ እኮ ፡ እውራሲ ፡ አላ ፡ መጋቢ ፡ እስመ ፡ ክልኤሆሙ ፡ አሣሤ ፡ ኢይትበሀሉ ።



ርታ ፡ እድርጎ ፡ ይተወው ። ከታዘዘበት ፡ ሹመት የሚሻርበትን ፡ ይነግረው ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ደዌ ፡ እንደ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ እሥራት ፡ ዕሩቅ ፡ እገር ፡ እንደመሄድ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ስደት ፡ ያለ ፡ ቢሆን ፡ በሥራዉ ፡ የታመነ ፡ የሚጠቅም ፡ ሹም ፡ ከበታቹ ፡ ካልሾመ ፡ ወይም የታወቀውን ፡ ትእዛዝ ፡ ለመያዝ ፡ ምልክት ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ይጸና ፡ ዘንድ ፡ ካልሾመ ። ካስወጣውም ፡ በኋላ ፡ እዛዥ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ሊመለስ ፡ እይገባውም ። አስቀድሞ ፡ በተጠቀሰው ፡ መውጣትስ ፡ በዳኛ ፡ ትእዛዝ ፡ ተመልሶ ፡ እዛዥ ሊሆን ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ፪፻ ፶፫ ያስተዳድርበት ፡ ዘንድ ፡ ዳኛ ፡ የሾመው ፡ ሰው ፡ በሃይማኖቱ ፡ ፍጹም ፡ የታመነ ፡ የሚጠቅም ፡ ቢሆን ፡ ከታዘዘለት ፡ ሰው ፡ ከዘመዶቹ ፡ ወገን ፡ ቢሆንም ፡ የሚገባው ፡ እርሱ ፡ ነው ። ለዘመዶች ፡ ከዘመዶች ፡ ጋራ ፡ ይሥራበት ። ቅርብ፡ ነውና ፡ ለቅርቡ ፡ ይሁን ።

፩ሺ፪፻ ፶፬ መከ ፡ ፲፮ ። ትእዛዙን ፡ በመጻፍ ፡ ላይና ፡ በገንዘቡ ፡ ላይ ፡ ልጁን ፡ ያሠለጥን ፡ ዘንድ ፡ ለሰው፡ ይገባዋል ። በተወዉ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ይሁን ።

፩ሺ፪፻ ፶፭ ፲፫ ። በተወዉ ፡ ላይ ፡ ባሪያውን ፡ ሊሾም ፡ መብት ፡ አለው ። እርሱ ፡ የሚሠራውን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ይሥራ ።

፩ሺ፪፻ ፶፮ ፲፬ ። ሴት ፡ ለልጇ ፡ ልጆች ፡ ትእዛዝ ፡ ብትጽፍ ፡ መጋቢ ፡ ጠባቂ ፡ ትሾምላቸው ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣን ፡ የላትም ። በዚህ ፡ ለአባታቸው ፡ ይገባዋልና ። አባት ፡ ባይኖራቸው ፡ ግን ፡ መጋቢና ፡ ጠባቂ ፡ ይሾምላቸው ። ዳግመኛም ፡ ብቻ ወላቸው ፡ ገንዘብ ፡ ብቻ ፡ መጋቢና ፡ የሚጠብቅላቸው ፡ ትሾምላቸው ፡ ዘንድ ፡ ለእርሷ ፡ ይገባታል ።

፩ሺ፪፻ ፶፯ መከ ፡ ፲፯ ። ትእዛዙን ፡ ሳይጽፍ ፡ የሞተ ፡ ሰው ፡ ልጆቹን ፡ ቢተው ፡ ልጆቹና ፡ ወንድሞቹም ፡ ቢቀሩ ፡ በርስቱ ፡ ማዘዝ ፡ ለወላጆቹ ፡ ይሁን ። በታዘዘለት ፡ ሰው ፡ እምሳያ ፡ ያስተዳድሩበት ። ከልጆች ፡ ጋራ ፡ ይካፈሉ ፡ ዘንድ ፡ ለወንድሞቹ ፡ እግባብ ፡ እይደለም ። ወላጆችንም ፡ ሊቃወሟቸው ፡ እይገባቸውም ። እዛዥ ፡ በዚህ፡ ይታወቃል ። ሹም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እውራሽ ፡ እይደለም ። ሁለቱም ፡ እዛዥ ፡ እይባሉምና ።

አንቀጽ ፡ ፵፩ ።

፩ሺ፪፻፺፰ መከ ፡ ፫ቱ ፡ ወእመቦ ፡ ዘጸሐፈ ፡ ውስተ ፡ ትእዛዙ ፡ ስሞ ፡ ለዘይኤዝዝ ፡ ሎቱ ፡ ወስሞ ፡ ለዘይሜግቦ ፡ ይንሥኡ ፡ ንዋያቲሆሙ ፡ ወይከፍልዎሙ ፡ ለውሉዱ ፡ ወኢይንሣእ ፡ እምኔሁ ፡ መጋቢ ። ወለእመ ፡ ኢጸሐፈ ፡ አዛዚ ፡ መጽሐፈ ፡ ትእዛዝ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘአዘዘ ፡ ሎሙ ፡ እኁ ፡ ዘኀለፈ ፡ እመዋዕሊሁ ፡ ወኮኖ ፡ ፳ወ፭ቱ ፡ ዓመት ፡ ውእቱኬ ፡ ይኩን ፡ መጋቤ ። ወለእመ ፡ አልቦሙ ፡ እኁ ፡ ዘየበቊ ፡ ይኩን ፡ መጋቤ ፡ ወኰናኔ ፡ ውእቱኬ ፡ ልብው ፡ እምአኃወ ፡ አቡሆሙ ፡ ወያስተዋፅእ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ እምንዋይ ፡ ዘንደገ ፡ አቡሆሙ ፡ በከመ ፡ ይደሉ ፡ ወይጽሐፍ ፡ ኵሎ ፡ ዘንደገ ፡ አቡሆሙ ፡ ወለይኩን ፡ ዕቁበ ፡ ኀበ ፡ መጽሐፍ ።

፩ሺ፪፻፺፱ ወለእመ ፡ አልቦሙ ፡ አኃወ ፡ አብ ፡ ልብዋን ፡ ዘኮነ ፡ ልብወ ፡ እምውሉደ ፡ አኃወ ፡ አቡሆሙ ፡ ዘኀለፈ ፡ መዋዕሊሁ ፡ እም፳ወ፭ቱ ፡ ዓመት ፡ ይመግብ ፡ ሕይወቶሙ ፡ ወለእመ ፡ አልቦሙ ፡ ውሉድ ፡ ለአኃወ ፡ አቡሆሙ ፡ ወፈቀደት ፡ እሞሙ ፡ ለውሉድ ፡ ከመ ፡ ትሥራዕ ፡ ግብረተሆሙ ፡ ትንግሮ ፡ ለፈታሒ ፡ እንከ ፡ ወፈታሒኒ ፡ ይንሣእ ፡ ቃለ ፡ ብፅዓት ፡ እምኔሃ ፡ ከመ ፡ ይእቲ ፡ ኢትትወሰብ ፡ እስከ ፡ ታልህቆሙ ፡ ለውሉዳ ፡ ወሶበ ፡ ልህቁ ፡ ተሀብ ፡ ሎሙ ፡ ርስቶሙ ።

፩ሺ፫፻ ወለእመ ፡ ኢፈቀደት ፡ ሕግ ፡ ትኤዝዝ ፡ ከመ ፡ ይሢሙ ፡ ሊቃናተ ፡ ሀገር ፡ ለደካትም ፡ መጋብተ ፡ ወአዛዝያነ ፡ ወይሰነአውዎሙ ፡ ላዕለ ፡ ዓስብ ፡ እምርስት ፡ በከመ ፡ መጠነ ፡ ንዋየ ፡ ርስት ፡ ዘተንደገት ፡ ወይንሥኡ ፡ እምኔሆሙ ፡ መጋብት ፡ ኵሎ ፡ ዘወሀብዎሙ ፡ ወይዕቀቡ ፡ ንዋየ ፡ ደካትም ፡ በኵሉ ፡ ጸሀቆሙ ፡ እስከ ፡ ይሁብዎሙ ፡ በጊዜ ፡ ብጽሐቶሙ ። ወለዘሂ ፡ ረሰዮ ፡ አዛዚ ፡ መጋቤ ፡ ወኰናኔ ፡ ኢይኅሥሥ ፡ እምኔሁ ፡ ተሐባዪ ፡ በዘአመገበ ፡ እስመ ፡ እግዚእ ፡ ንዋይ ፡ ለሊሁ ፡ ውእቱ ፡ ዘረሰዮ ፡ መጋቤ ፡ ቀዳሚ ፡ ላዕለ ፡ ወልዱ ፡ ወንዋዩ ፡ እስከ ፡ ይልህቅ ።

፩ሺ፫፻፩ መከ ፡ ፱ቱ ፡ ወሕፃናኒ ፡ ይኩኑ ፡ እስከ ፡ የኀልፍ ፡ እምሕይወቱ ፡ ፲ወ፬ቱ ፡ ዓመት ፡ ወወለትኒ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ዓመት ፡ ታሕተ ፡ እዴሁ ፡ ለመጋቤ ። ወእምከመ ፡ ኀለፈ ፡ ዝንቱ ፡ ዕድሜ ፡ ይፃኡ ፡ እምሥልጣኑ ፡ ወእምዝ ፡ ይኩኑ ፡

በገንዘቡ ፡ ስለሚያዝዝ ።

፩ሺ፪፻፺፰ መከ ፡ ፫ ። በትእዛዙ ፡ ውስጥ ፡ የሚያዝዝለትን ፡ ሰው ፡ ስምና ፡ የሚያስተዳድረውን ፡ ሰው ፡ ስም ፡ የጻፈ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ተቀብለው ፡ ለልጆቹ ፡ ያካፍሏቸው ። ሹሙም ፡ ከእርሱ ፡ አይውሰድ ። አዛዥ ፡ የትእዛዝ ፡ መጽሐፍ ፡ ባይጽፍ ፡ የሕፃንነቱ ፡ ወራት ፡ ያለፈው ፡ ፳፭ ፡ ዓመት ፡ የሆነው ፡ ያዘዘላቸው ፡ ወንድም ፡ ቢኖር ፡ እርሱ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ይሁን ። ታላቅ ፡ ወንድም ፡ ባይኖራቸው ፡ ከአባታቸው ፡ ወንድሞች ፡ አስተዋይ ፡ የሆነው ፡ አስተዳዳሪና ፡ ፈራጅ ፡ ይሁን ፡ አባታቸው ፡ ከተወው ፡ ገንዘብ ፡ እንደሚገባ ፡ ለእነርሱ ፡ ያወጣጣ ። አባታቸው ፡ የተወውን ፡ ሁሉ ፡ ይጻፍ ፡ በመዝገብም ፡ የተጠበቀ ፡ ይሁን ።

፩ሺ፪፻፺፱ አስተዋዮች ፡ የሆኑ ፡ የአባት ፡ ወንድሞች ፡ ባይኖሯቸው ፡ ከአባታቸው ፡ ወንድሞች ፡ ልጆች ፡ ወገን ፡ አስተዋይ ፡ የሆነው ፡ ዘመኑ ፡ ከ፳፭ ፡ ዓመት ፡ ያለፈ ፡ ያስተዳድራቸው ። ለአባታቸው ፡ ወንድሞች ፡ ልጆች ፡ ባይኖሯቸው ፡ የልጆቹ ፡ እናት ፡ ሥራቸውን ፡ (ገንዘባቸውን ፡ ) ልታከናውን ፡ ብትወድ ፡ እንግዲህ ፡ ለዳኛ ፡ ትንገረው ። ዳኛውም ፡ ልጆቿን ፡ እስከታሳድጋቸው ፡ ድረስ ፡ ባል ፡ እንዳታገባ ፡ ባደጉም ፡ ጊዜ ፡ ርስታቸውን ፡ እንድትሰጣቸው ፡ የመሐላ ፡ ቃል ፡ ይቀበላት ።

፩ሺ፫፻ እርሷ ፡ ባትወድ ፡ ግን ፡ የሀገር ፡ ዳኞች ፡ ለድሃ ፡ አደጎች ፡ አስተዳዳሪዎችንና ፡ አዛዦችን ፡ ይሹሙ ፡ ዘንድ ፡ ሕጋችን ፡ ታዝዛለች ። እንደ ፡ ተተወችው ፡ የርስት ፡ ገንዘብ ፡ መጠን ፡ በታወቀች ፡ ደመወዝ ፡ ይስማሙላቸው ። ሹማምቱም ፡ የሰጧቸውን ፡ ሁሉ ፡ ከእነርሱ ፡ ይቀበሉ ። አካለ ፡ መጠን ፡ ባደረሱ ፡ ጊዜ ፡ እስከሚሰጧቸው ፡ ድረስ ፡ የድሃ ፡ አደጎችን ፡ ገንዘብ ፡ በፍጹም ፡ ትጋት ፡ ይጠብቁ ። አዛዥ ፡ ሞግዚትና ፡ ሹም ፡ ካደረገው ፡ ሰው ፡ በሾመበት ፡ ገንዘብ ፡ ላይ ፡ ዋስ ፡ አይፈልግ ። የገንዘቡ ፡ ጌታ ፡ እስኪያድግ ፡ ድረስ ፡ አስቀድሞ ፡ በገንዘቡና ፡ በልጁ ፡ ላይ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ያደረገው ፡ እርሱ ፡ ነውና ።

፩ሺ፫፻፩ መከ ፡ ፱ ። ወንድ ፡ ልጅም ፡ ከዕድሜው ፡ ፲፬ ፡ ዓመት ፡ ሴት ፡ ልጅም ፡ ፲፪ ፡ ዓመት ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ በሞግዚት ፡ እጅ ፡ ሥር ፡ ይሁኑ ። ይህ ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ከሥልጣኑ ፡ ይውጡ ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ፳፭ ፡ ዓመት ፡ እስኪሆናቸው ፡

ታሕተ ፡ እዴሁ ፡ ለኰናኒ ፡ እስከ ፡ ይከውን ፡ ሎሙ ፡ ፳ወ፩ቱ ፡ ዓመት ፡ ወይእተ ፡ ጊዜ ፡ ይኩን ፡ ሎሙ ፡ መባሕት ፡ ላዕለ ፡ ግብረ ፡ ዚአሆሙ ።

፩ሺ፫፻፶፱ ወኀዲገ ፡ ምግብና ፡ ይኩን ፡ በ፪ቱ ፡ ቃላት ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘ፲ወ፩ቱ ፡ ወዘኮነ ፡ ሎቱ ፡ ለብእሲ ፡ ፳ቱ ፡ ውሉድ ፡ ተባዕት ፡ ወአንስት ፡ ወፈቀደ ፡ ከመ ፡ ይድኅን ፡ እምሢመተ ፡ ትእዛዝ ፡ ወከመ ፡ ኢይኩን ፡ መጋቤ ፡ ለደካትም ፡ ነኪራን ፡ ወኢለእዝማድ ፡ ይደልዎ ፡ ዝንቱ ። ወእመሰ ፡ ኮኑ ፡ ሎቱ ፡ ዘይውሕዱ ፡ እም፳ቱ ፡ ውሉድ ፡ ያገብሮ ፡ ፈታሒ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ መጋቤ ፡ አው ፡ ኰናኔ ፡ ለደከታም ፡ እምእዝማዲሁ ፡ ወካልአኒሆሙ ።

፩ሺ፫፻፷ ወዓዲ ፡ ዘ፪ት ፡ እመቦ ፡ ብእሲ ፡ ዘኮነ ፡ መጋቤ ፡ ለደካትም ፡ ኢይደልዎ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይድኅን ፡ እምትእዛዘ ፡ መጽሐፍ ፡ ወእምግብር ፡ ዘተአዘዘ ፡ ሎቱ ፡ በንዋዮሙ ፡ ለእመ ፡ ተወከፈ ፡ መጽሐፈ ፡ ትእዛዝ ፡ ወተዳደቀ ፡ ድድቅ ፡ ለውእቱ ፡ ንዋይ ።

፩ሺ፫፻፷፩ ዘ፪ወ፫ቱ ፡ ወይደልዎ ፡ ለመጋቤ ፡ ደካትም ፡ ከመ ፡ ያመግብ ፡ ብእሴ ፡ በእንተ ፡ ፈጽሞ ፡ ንዋያቲሆሙ ፡ ባሕቱ ፡ በትእዛዘ ፡ ፈትሒ ፡ ይኩን ።

፩ሺ፫፻፷፪ መጅ ፡ ፲ወ፩ቱ ፡ ወለእመኒ ፡ ተዐውቀ ፡ ከመ ፡ ዘእመገብዎ ፡ በጽሒፍ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ተዐደወ ፡ ላዕለ ፡ ደካትም ፡ ወኢተዘከረ ፡ ለምዕቅብና ፡ ለይኩን ፡ ርስት ፡ ዘተኀድገ ፡ ውስተ ፡ እደዊሆሙ ፡ ለመገብተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እስከ ፡ ይልህቁ ፡ ወኢያብሖ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእለ ፡ ይሠየሙ ፡ መገብት ፡ ላዕለ ፡ ዘውስተ ፡ እደዊሆሙ ፡ ከመ ፡ ያስተዋዕእዎ ፡ በዘኢመፍትው ፡ ወከመ ፡ የሐርትሙ ፡ ውሉደ ፡ አዛዚ ።

፩ሺ፫፻፷፫ መከ ፡ ፯ቱ ፡ ወኢይደልዎ ፡ ለዘእመገብዎ ፡ አው ፡ ለዘሜጥዎ ፡ ከመ ፡ ይሢጥ ፡ ምንተኒ ፡ እምንዋየ ፡ ደካትም ፡ ወየሀብ ፡ ጸባሕተ ፡ አው ፡ ሊቀሐ ፡ ዘእንበለ ፡ መባሕተ ፡ ፈታሒ ፡ ወአገዘኦቱ ፡ ቦቱ ፡ ከመ ፡ ይሢጥ ፡ ወይእተ ፡ ጊዜ ፡ ይሢጥ ፡ በእምጣነ ፡ ጸባሕት ፡ ወሊቃሕ ።

፩ሺ፫፻፷፬ ዘ፯ ፡ ወዘሂ ፡ ኮነ ፡ እምሐራ ፡ ወላእካነ ፡ ንጉሥ ፡ ኢይሠየም ፡ ለምዕቅብና ፡ ወኢለምግብና ፡ ላዕለ ፡ ደካትም ፡ ለእመ ፡ ኢተፈልጠ ፡ እመልእክተ ፡ ንጉሥ ። ወነገርሰ ፡ በእንተ ፡ ትእዛዘ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ወመነኮሳት ፡ ወእግብርት ፡ ወግ

ድረስ ፡ በሹም ፡ እጅ ፡ ይሁኑ ። ያንጊዜ ፡ በሥራቸው ፡ ላይ ፡ መብት ፡ ይኑራቸው ።

፩ሺ፫፻፶፱ ሹመትን ፡ መተው ፡ በ፪ ፡ ነገር ፡ ይሁን ። ከእነርሱም ፡ አንዱ ፡ ፲፩ ። አምስት ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ያሉት ፡ ሰው ፡ ከትእዛዝ ፡ ሹመት ፡ እንዲድን ፡ ለባዕድና ፡ ለዘመድ ፡ ድኃ ፡ አደግ ፡ ልጆች ፡ አስተዳዳሪ ፡ እንዳይሆን ፡ ቢወድ ፡ ይህ ፡ ይገባዋል ። ከ፭ ፡ ልጆች ፡ የሚያንሱ ፡ ቢሆኑለት ፡ ግን ፡ ከዘመዶቹ ፡ ወይም ፡ ከሌሎች ፡ ቢሆኑ ፡ ለድኃ ፡ አደጎች ፡ ልጆች ፡ ሞግዚት ፡ ወይም ፡ ሹም ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ዳኛ ፡ ይከፈል ።

፩ሺ፫፻፷ ዳግመኛም ፡ ፪ ። ለድኃ ፡ አደጎች ፡ ልጆች ፡ መጋቢ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ከደብዳቤ ፡ ትእዛዝ ፡ በገንዘባቸውም ፡ ከታዘዘለት ፡ ሥራ ፡ ሊድን ፡ አይገባውም ። የትእዛዙን ፡ ደብዳቤ ፡ ከተቀበለና ፡ ያነን ፡ ገንዘብ ፡ ድንገት ፡ አደጋ ፡ ካገኘው ፡ ይከፈለው ።

፩ሺ፫፻፷፩ ፪፫ ። የድኃ ፡ አደጎች ፡ ሹም ፡ ገንዘባቸውን ፡ ስለመጠበቅ ፡ ሰው ፡ ሊሾም ፡ ይገባዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ በዳኛ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሁን ።

፩ሺ፫፻፷፪ መጅ ፡ ፲፩ ። በጽሕፈት ፡ የሾሙት ፡ ሰው ፡ በድኃ ፡ አደጎች ፡ ላይ ፡ እንደተላለፈና ፡ አደራውን ፡ እንደአላሰባት ፡ ቢታወቅ ፡ እስኪያድጉ ፡ ድረስ ፡ የተተወው ፡ ርስት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሹማምንት ፡ እጅ ፡ ይሁን ። በእጃቸው ፡ ያለውን ፡ ገንዘብ ፡ በማይገባ ፡ ያወጣጡት ፡ ዘንድ ፡ ያዛዥንም ፡ ልጆች ፡ ይበድሉ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሚሾሙ ፡ ሹማምት ፡ አላሰናበተም ።

፩ሺ፫፻፷፫ መከ ፡ ፯ ። አስተዳዳሪ ፡ ላደረጉት ፡ ወይም ፡ ለሾሙት ፡ ሰው ፡ ያለዳኛ ፡ ፈቃድ ፡ ከድኃ ፡ አደጎች ፡ ገንዘብ ፡ ምንምን ፡ ሊሸጥ ፡ ግብር ፡ ወይም ብድር ፡ ሊሰጥ ፡ አይገባውም ። እንዲሸጥ ፡ እርሱን ፡ ቢያዝዘውም ፡ ያንጊዜ ፡ ለብድሩና ፡ ለግብሩ ፡ ያህል ፡ ይሸጥ ።

፩ሺ፫፻፷፬ ፯ ። ከንጉሥ ፡ ጭፍራና ፡ ወታደሮች ፡ ወገን ፡ የሆነም ፡ ከንጉሥ ፡ አገልግሎት ፡ ካልተለየ ፡ በድኃ ፡ አደጎች ፡ ላይ ፡ ለመጠበቅና ፡ ለማስተዳደር ፡ አይሾም ። ስለኤጲስ ፡ ቆጶሳትና ፡ ስለመነኮሳት ፡ ነፃ ፡ ስለወጡና ፡ ስላልወጡ ፡ ባሮች

አንቀጽ ፡ ፵፱ ።

በዛን ፡ ተነግረ ፡ ዘፍጻሜሁ ፡ ለአንቀጸ ፡ ተዋ
ርሶ ።

፩ሺ፫፻፶፰ ሥርዋጽ ፡ ናሁ ፡ ተሠርዐት ፡ ሥርዓተ ፡ ተዋ
ርሶ ፡ በምክረ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ቄርሎስ ፡
ወኤጲስቆጶሳቲሁ ፡ ካልእ ፡ እምዘተነግረ ፡ በዝ
ንቱ ፡ አንቀጽ ፡ ወይእቲኬ ፡ ድሉት ፡ እስመ ፡
ይእቲ ፡ ተሠርዐት ፡ ካዕበ ፡ እምኅበ ፡ መንፈቆ
ሙ ፡ ለሊቃነ ፡ ጳጳሳቲነ ፡ እለ ፡ ቀደሙ ፡ እም
ኅበ ፡ ማእምራን ፡ ካዕበ ፡ ወበላዕሌሃ ፡ ያስምኩ ።

ስለ ፡ ርስት ።

ትእዛዝ ፡ ነገርስ ፡ በአንቀጸ ፡ ተዋርሶ ፡ ተነግ
ሯል ።

፩ሺ፫፻፶፰ ሥርዋጽ ። እነሆ ፡ ያወራረስ ፡ ሥርዓት ፡
በሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ በአባ ፡ ቄርሎስና ፡ በኤጲስ ፡
ቆጶሳቱ ፡ እስተያየት ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ከተነገ
ረው ፡ ሌላ ፡ ተጽፋለች ። ይህችውም ፡ የተገባች
ናት ። ከቀደሙት ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ከእኩሌ
ቶች ፡ ዘንድ ፡ ዳግመኛም ፡ ከዐዋቆች ፡ ዘንድ ፡
ተጽፋለችና ። በእርሷም ፡ ይጸናሉ ፡ (ጸንተው ፡
ይኖራሉ) ።

## አንቀጽ ፡ ፵ወ፪ቱ ፡

### በእንተ ፡ ርስት ።

፩ሺ፫፻፶፱ ወውእቱ ፡ ፲ወ፫ቱ ፡ ምዕራፍ ። ምዕራፍ ፡ ቀዳ
ማዊ ፡ በእንተ ፡ ዘይቀድም ፡ ገቢሮቱ ፡ ውስተ ፡
ኅድገት ፡ ወውእቱ ፡ ዘይትረከብ ፡ እምንዋዩ ፡
ለዘሞተ ፡ ወእማሬ ፡ ዕሴታት ፡ እንተ ፡ ይትከ
ልኡ ፡ ቦቶን ፡ ወራስያን ፡ እምነ ፡ ተኃሣሥያን፡
በርስቶሙ ።

፩ሺ፫፻፷ መከ ፡ ፴ወ፩ቱ ፡ ያቅድሙ ፡ ሤጠ ፡ ግንዘቱ ፡
ወዓስበ ፡ እለ ፡ ይከርዩ ፡ ወሤጠ ፡ መቃብር ።
ጠስ ፡ ፴ወ፪ቱ ፡ ወእስተዋፅኦተ ፡ ግንዘቱ ፡ ወዘ
ይተልዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ሥርዓተ ፡ ቍርባን ፡
እሙር ። ወነዋ ፡ ተነግረ ፡ በአንቀጸ ፡ ሙታን ።

፩ሺ፫፻፷፩ ረስጣ ፡ ፸ወ፱ቱ ፡ ሀቡ ፡ ለነዳያን ፡ እምጥሪ
ቶቱሁ ፡ ለዘሞተ ፡ ከመ ፡ ይኩኖ ፡ ተዝካረ ፡ ለር
እሱ ።

፩ሺ፫፻፷፪ ሥርዋጽ ፡ ዘሀሎ ፡ ውስተ ፡ ቀኖናት ፡ ዘሐዋ
ርያ ፡ ትእዛዘ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወጳውሎስ ፡ ወያዕ
ቆብ ፡ ወይመጽውቱ ፡ ለምስኪናን ፡ እምንዋ
ዮሙ ፡ ለእለ ፡ ኖሙ ፡ እምእመናን ፡ ኄራን ፡
ወእኩ ፡ ዘከሐዲያን ፡ እኩያን ። ወከማሁ ፡ ዘ፳ ፡
ነበረ ፡ ውስተ ፡ ቀኖናተ ፡ ነገሥት ፡ ይደልዎ ፡
ለዘበጽሐቶ ፡ ዕለተ ፡ ሞቱ ፡ ከመ ፡ የአዝዝ ፡
ለጸኑሳን ፡ እምንዋዩ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ሎቱ ፡
ሶማት ፡ በዕለተ ፡ ፍዳ ፡ ወኢይደልዎ ፡ ለዘእሲ ፡
ዘእንበለ ፡ ዘአቅረቦ ፡ እምጽድቅ ።

፩ሺ፫፻፷፫ መከ ፡ ዘ፺ኛ፰ቱ ፡ እምዝኒ ፡ ዘሀሎ ፡ ላዕለ ፡
ምዉት ፡ እምጸባሕት ፡ ወዕዳ ። ዘ፪ወ፹ወ፫ቱ ፡
ዘ፪ወ፹ወ፭ቱ ፡ መጅ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ወእመሰ ፡ ኮነ ፡
ንዋይ ፡ ዘኅደገ ፡ ዘኢየአክል ፡ ለፈድዮ ፡ ልቃሕ ፡

## አንቀጽ ፡ ፵፪

### ስለርስት ፡ ይናገራል ።

፩ሺ፫፻፶፱ ይኸውም ፡ ፲፫ ፡ ምዕራፍ ፡ ነው ። መጀመሪያ ፡
ምዕራፍ ፡ በመተው ፡ ሊያደርጉት ፡ ስለሚቀድ
መው ፡ ይናገራል ። ይኸውም ፡ ከሙት ፡ ገንዘብ
የሚገኝ ፡ ነው ። ወራሾችም ፡ ርስታቸውን ፡ ከሚ
ፈላስጉት ፡ የሚከለከሉባቸውን ፡ ዕሴታት ፡ ማመ
ልከት ፡ ነው ።

፩ሺ፫፻፷ መክ ፡ ፴፩ ። የመግነዙን ፡ ዋጋና ፡ የመቃብር ፡
ቆፋሪዎችን ፡ ደመወዝ ፡ የመቃብሩንም ፡ ዋጋ ፡
ያስቀድሙ ። ጠስ ፡ ፴፪ ። ስመግነዙ ፡ የሚወጣ
ጣውና ፡ ይህን ፡ የሚከተለው ፡ የታወቀው ፡
የቍርባኑ ፡ ሥርዓት ፡ እነሆ ፡ በአንቀጸ ፡ ሙታን
ተነግሯል ። (ፍ ፡ ነ ፡ ፺፪ ፺፫) ።

፩ሺ፫፻፷፩ ረስጣ ፡ ፸፱ ። ለራሱ ፡ መታሰቢያ ፡ ይሆነው ፡
ዘንድ ፡ ከሞተው ፡ ሰው ፡ ገንዘብ ፡ ለነዳያን ፡
ስጡ ።

፩ሺ፫፻፷፪ ሥርዋጽ ። በሐዋርያት ፡ መጽሐፍ ፡ ያለ ፡ የጴ
ጥሮስና ፡ የጳውሎስ ፡ የያዕቆብም ፡ ትእዛዝ ።
የከፉዎች ፡ ከሐዲዎችን ፡ ያይደለ ፡ ከደጋጎቹ ፡
ምእመናን ፡ ወገን ፡ ከሞቱት ፡ ሰዎች ፡ ገንዘብ ፡
ለድሆች ፡ ይመጽውቱ ። እንደዚሁም ፡ ፳ ።
በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ተጽፏል ። ዕለተ ፡ ሞቱ ፡
ለደረሰችበት ፡ ሰው ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ዋጋ ፡ ይሆ
ንለት ፡ ዘንድ ፡ ከገንዘቡ ፡ ለድሆች ፡ ሊያዝዝ ፡
ይገባዋል ። ከእውነት ፡ ወገን ፡ ያቀረበው ፡ ካል
ሆነ ፡ በቀር ፡ ለሰው ፡ አይገባውም ።

፩ሺ፫፻፷፫ መክ ፡ ፺፰ ። ከግብርና ፡ ከዕዳ ፡ በመዋቲ ፡
ላይ ፡ ያለውም ፡ የሚከፈለው ፡ ከዚህ ፡ ነው ።
፪፹፫ ። ፪፹፭ ። መጅ ፡ ፲፪ ። የተወው ፡ ገንዘብ ፡
ብድር ፡ ለመክፈል ፡ የማይበቃ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡

አንቀጽ ፡ ፵፪ ።

ዑሣን ፡ ተነግረ ፡ በፍጻሜሁ ፡ ለአንቀጸ ፡ ተዋ
ርሶ ።

፩ሺ፫፻፺፰ ሥርዋጽ ፡ ናሁ ፡ ተሠርዐት ፡ ሥርዓተ ፡ ተዋ
ርሶ ፡ በምክረ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ቄርሎስ ፡
ወኤጲስቆጶሳቲሁ ፡ ካልእ ፡ እምዘተነግረ ፡ በዝ
ንቱ ፡ አንቀጽ ፡ ወይእቲኬ ፡ ድሉት ፡ እስመ ፡
ይእቲ ፡ ተሠርዐት ፡ ካዕበ ፡ እምኀበ ፡ መንፈቆ
ሙ ፡ ለሊቃነ ፡ ጳጳሳቲነ ፡ እለ ፡ ቀደሙ ፡ እም
ኀበ ፡ ማእምራን ፡ ካዕበ ፡ ወበላዕሌሃ ፡ ያስምኩ ።

ስለ ፡ ርስት ።

ትእዛዝ ፡ ነገርስ ፡ በአንቀጸ ፡ ተዋርሶ ፡ ተነግ
ሯል ።

፩ሺ፫፻፺፰ ሥርዋጽ ። እነሆ ፡ ያወራረስ ፡ ሥርዓት ፡
በሊቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ በአባ ፡ ቄርሎስና ፡ በኤጲስ ፡
ቆጳሳቱ ፡ አስተያየት ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ከተነገ
ረው ፡ ሌላ ፡ ተጽፋለች ። ይህችውም ፡ የተገባች
ናት ። ከቀደሙት ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ከአኩሌ
ቶች ፡ ዘንድ ፡ ዳግመኛም ፡ ከዐዋቆች ፡ ዘንድ ፡
ተጽፋለችና ። በእርሷም ፡ ይጸናሉ ፡ (ጸንተው ፡
ይኖራሉ) ።

---

## አንቀጽ ፡ ፵ወ፪ቱ ፡

### በእንተ ፡ ርስት ።

፩ሺ፫፻፺፱ ወውእቱ ፡ ፲ወ፫ቱ ፡ ምዕራፍ ። ምዕራፍ ፡ ቀዳ
ማዊ ፡ በእንተ ፡ ዘይቀድም ፡ ኀቢሮቱ ፡ ውስተ ፡
ኀድገት ፡ ወውእቱ ፡ ዘይትረከብ ፡ እምንዋዩ ፡
ለዘሞተ ፡ ወእማሬ ፡ ዕለታት ፡ እንተ ፡ ይትከ
ልኡ ፡ ቦቱን ፡ ወራሰያን ፡ እምነ ፡ ተኃሣሥያን፡
በርስቶሙ ።

፩ሺ፫፻፺፲ መክ ፡ ፴ወ፩ቱ ፡ ያቅድሙ ፡ ሤጠ ፡ ግንዘቱ ፡
ወዓስበ ፡ እለ ፡ ይከርዩ ፡ ወሤጠ ፡ መቃብር ።
ጠስ ፡ ፴ወ፪ቱ ፡ ወእስተዋፅኦተ ፡ ግንዘቱ ፡ ወዘ
ይተልዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ሥርዓተ ፡ ቍርባን ፡
እሙር ። ወነዋ ፡ ተነግረ ፡ በአንቀጸ ፡ ሙታን ።

፩ሺ፫፻፺፲፩ ረስጣ ፡ ፳ወ፱ቱ ፡ ሀቡ ፡ ለነዳያን ፡ እምጥሪ
ታቲሁ ፡ ለዘሞተ ፡ ከመ ፡ ይኩኖ ፡ ተዝካረ ፡ ለር
እሱ ።

፩ሺ፫፻፺፲፪ ሥርዋጽ ፡ ዘሀሎ ፡ ውስተ ፡ ቀኖናት ፡ ዘሐዋ
ርያ ፡ ትእዛዘ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወጳውሎስ ፡ ወያስ
ቆብ ፡ ወይመጽውቱ ፡ ለምስኪናን ፡ እምንዋ
ዮሙ ፡ ለእለ ፡ ኖሙ ፡ እምእመናን ፡ ኄራን ፡
ወእኩ ፡ ዘከሐድያን ፡ እኩያን ። ወከማሁ ፡ ዘ፰ ፡
ነበረ ፡ ውስተ ፡ ቀኖናተ ፡ ነገሥት ፡ ይደልዎ ፡
ለዘበጽሐቶ ፡ ዕለተ ፡ ሞቱ ፡ ከመ ፡ የአዝዝ ፡
ለጽኑሳን ፡ እምንዋዩ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ሎቱ ፡
ዕሤት ፡ በዕለተ ፡ ፍዳ ፡ ወኢይደልዎ ፡ ለብእሲ ፡
ዘእንበለ ፡ ዘአቅረቦ ፡ እምጽድቅ ።

፩ሺ፫፻፺፲፫ መክ ፡ ዘ፺ወ፰ቱ ፡ እምዝኒ ፡ ዘሀሎ ፡ ላዕለ ፡
ምዉት ፡ እምጸባሕት ፡ ወዕዳ ። ዘ፻ወ፳ወ፫ቱ ፡
ዘ፻፳ወ፭ቱ ፡ መጅ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ወእመሰ ፡ ኮነ ፡
ንዋይ ፡ ዘኀደገ ፡ ዘኢየአክል ፡ ለፈድዮ ፡ ሊቃሕ ፡

## አንቀጽ ፡ ፵፪

### ስለርስት ፡ ይናገራል ።

፩ሺ፫፻፺፱ ይኸውም ፡ ፲፫ ፡ ምዕራፍ ፡ ነው ። መጀመሪያ ፡
ምዕራፍ ፡ በሙተው ፡ ሊያደርጉት ፡ ስለሚቀድ
መው ፡ ይናገራል ። ይኸውም ፡ ከሙት ፡ ገንዘብ
የሚገኝ ፡ ነው ። ወራሾችም ፡ ርስታቸውን ፡ ከሚ
ፈላለጉት ፡ የሚከለከሉባቸውን ፡ ዕለታት ፡ ማመ
ልከት ፡ ነው ።

፩ሺ፫፻፺፲ መክ ፡ ፴፩ ። የመግነዙን ፡ ዋጋና ፡ የመቃብር ፡
ቆፋሪዎችን ፡ ደመወዝ ፡ የመቃብሩንም ፡ ዋጋ ፡
ያስቀድሙ ። ጠስ ፡ ፴፪ ። ለመግነዙ ፡ የሚወጣ
ጣውና ፡ ይህን ፡ የሚከተለው ፡ የታወቀው ፡
የቍርባኑ ፡ ሥርዓት ፡ እነሆ ፡ በአንቀጸ ፡ ሙታን
ተነግሯል ። (ፍ ፡ ነ ፡ ፯፻ ፺፫) ።

፩ሺ፫፻፺፲፩ ረስጣ ፡ ፳፱ ። ለራሱ ፡ መታሰቢያ ፡ ይሆነው ፡
ዘንድ ፡ ከሞተው ፡ ሰው ፡ ገንዘብ ፡ ለነዳያን ፡
ስጡ ።

፩ሺ፫፻፺፲፪ ሥርዋጽ ። በሐዋርያት ፡ መጽሐፍ ፡ ያለ ፡ የጴ
ጥሮስና ፡ የጳውሎስ ፡ የያዕቆብም ፡ ትእዛዝ ።
የከፉዎች ፡ ከሐዲዎችን ፡ ያይደለ ፡ ከደጋጎቹ ፡
ምእመናን ፡ ወገን ፡ ከሞቱት ፡ ሰዎች ፡ ገንዘብ ፡
ለድሆች ፡ ይመጽውቱ ። እንደዚሁም ፡ ፰ ።
በፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ተጽፏል ። ዕለተ ፡ ሞቱ ፡
ለደረሰችበት ፡ ሰው ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ዋጋ ፡ ይሆ
ንለት ፡ ዘንድ ፡ ከገንዘቡ ፡ ለድሆች ፡ ሊያዝዝ ፡
ይገባዋል ። ከእውነት ፡ ወገን ፡ ያቀረበው ፡ ካል
ሆነ ፡ በቀር ፡ ለሰው ፡ አይገባውም ።

፩ሺ፫፻፺፲፫ መክ ፡ ፺፰ ። ከግብርና ፡ ከዕዳ ፡ በመዋቲ ፡
ላይ ፡ ያለውም ፡ የሚከፈለው ፡ ከዚህ ፡ ነው ።
፻፳፫ ። ፻፳፭ ። መጅ ፡ ፲፪ ። የተወው ፡ ገንዘብ ፡
ብድር ፡ ለመከፈል ፡ የማይበቃ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡

ወለእመ ፡ ኢነሥአ ፡ ወራሲ ፡ ኢይደልዎ ፡ ፈድዮ ፡ ዕዳ ፡ ወልቃሕ ፡ ወእመሰ ፡ ነሥአ ፡ ኪያሃ ፡ ይፍልጣ ፡ ወይጽሐፍ ፡ ኍልቈ ፡ ዚአሃ ፡ ወይክሥት ፡ ለሰብአ ፡ ልቃሕ ፡ ምጣኔሃ ፡ ወየሀብ ፡ ለኵሉ ፡ ለለ፩፩ ፡ እምኔሆሙ ፡ በሐሳበ ፡ ንዋዮሙ ። ወእመሰ ፡ ተወክፋ ፡ ወአስተዋፅኦ ፡ ኪያሃ ፡ በውሂብ ፡ ወበዘይመስሎ ፡ አው ፡ ኀብአ ፡ ወኢከሠተ ፡ ኪያሃ ፡ ፈቲዶ ፡ ተዓርቆቶሙ ፡ ለሰብአ ፡ ልቃሕ ፡ በእንተ ፡ ንዋዮሙ ። ወእመ ፡ ወሀቦሙ ፡ መንፈቀ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይፍድዮሙ ፡ ኵሎ ፡ ንዋዮሙ ፡ እምድኅረ ፡ ተጠየቀ ፡ በሰማዕት ፡ ጻድቃን ፡ ወመትልወ ፡ ዝንቱ ፡ ዘሀሎ ፡ ላዕለ ፡ ምውት ፡ እምነ ፡ ዕዳ ፡ አምላካዊ ፡ ዘከመ ፡ ብፅዓት ፡ ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ይግበሩ ፡ ትእዛዘ ፡ ሕግ ።

፩ሺ፫፻፲፬ ወናሁ ፡ አቅደምነ ፡ ነጊረ ፡ በእንተ ፡ አዛዚ ፡ ከመ ፡ ኢይደልዎ ፡ ሎቱ ፡ የአዝዝ ፡ በትእዛዙ ፡ ውስተ ፡ ንዋይ ፡ በዘይፈደፍድ ፡ እምነ ፡ መንፈቁ ፡ ወራብዕት ፡ እዴሁ ፡ ለዘይመልኮ ፡ ወይትርፍ ፡ ትርብዕት ፡ ለዘይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይረስ ፡ አልቦቱ ፡ በውስቴቱ ፡ አዝዞ ።

፩ሺ፫፻፲፭ ጠሰ ፡ ዘ፴ወ፩፩ ፡ ዘ፴ወ፯ቱ ፡ ወኢይደልዎ ፡ ለመኑሂ ፡ ከመ ፡ ይትኀሠሥዎሙ ፡ ለወራስያኒሁ ፡ ለዘሞተ ፡ አው ፡ ለሰብአ ፡ ዚአሁ ፡ አው ፡ ለእለ ፡ ተሐበዩዎ ፡ እምቅድመ ፡ ፍጻሜ ፡ ተሰዐ ፡ መዋዕል ፡ እንተ ፡ ቦቱን ፡ ይከውኑ ፡ ኅዙናን ። አው ፡ ያሕሥሞሙ ፡ በ፩፩ ፡ ገጽ ፡ እምገጻት ፡ አው ፡ ይሰዶሙ ፡ ኀበ ፡ መንበረ ፡ ፍትሕ ፡ ኢ ፡ በምክንያተ ፡ ልቃሕ ፡ ወዕዳ ፡ ዘሀሎ ፡ ላዕለ ፡ ዘአዕረፈ ፡ ወኢ ፡ በምክንያት ፡ ካልእ ፡ የአኀዞሙ ።

፩ሺ፫፻፲፮ ወለእመ ፡ ተኀበለ ፡ ፩፩ ፡ እምቅድመ ፡ ይፈጽሙ ፡ ተሰዐ ፡ መዋዕለ ፡ ወአኀዞ ፡ ለ፩፩ ፡ እምኔሆሙ ፡ አው ፡ ገብረ ፡ ላዕሌሁ ፡ ኀይለ ፡ በነሚአ ፡ ንዋዩ ፡ በምንትኒ ፡ አው ፡ በተሐብዮቱ ፡ ገዘንቱ ፡ ብጡል ፡ ውእቱ ። ወእምከመሰ ፡ ተፈጸመት ፡ ዕድሜ ፡ እንተ ፡ ተወሰነት ፡ ይደሉ ፡ እንከ ፡ ተጋእዞቶሙ ፡ በዘይደሉ ፡ በውስተ ፡ ሕግ ።

፩ሺ፫፻፲፯ ምዕራፍ ፡ ዳግማዊ ፡ በእንተ ፡ ነገረ ፡ ፍጻሜ ፡ ዘየጠይቅ ፡ ትእዛዘ ፡ ተዋርሶ ፡ ወሥርዓተ ፡ መዓርጋት ፡ ዘወራስያን ። ተዋርሶሰ ፡ ኀበ ፡ ፪ቱ ፡ ይትከፈል ፡ ፩፩ ፡ እምኔሆሙ ፡ ለዘተአዘዘ ፡



ወራሽም ፡ ባይወስድ ፡ ዕዳውንና ፡ ብድሩን ፡ መክፈል ፡ አይገባውም ። እርሷን ፡ ቢወስድ ፡ ግን ፡ ለይቶ ፡ ቍጥሯን ፡ ይጻፍ ። ለአበዳሪዎችም ፡ ልኩን ፡ ይግለጽ ። ለሁሉም ፡ ለእያንዳንዳቸው ፡ በገንዘባቸው ፡ ግምት ፡ ይስጥ ። እርሷን ፡ ተቀብሎ ፡ በመስጠትና ፡ በሚመስለው ፡ ቢያወጣጣት ፡ ወይም ፡ አበዳሪዎችን ፡ ስለገንዘባቸው ፡ ባዶ ፡ ሊያስቀራቸው ፡ ወድዶ ፡ ቢሸሽግ ፡ እርሷንም ፡ ባይገልጽ ፡ እኩሌታዋንም ፡ ቢሰጣቸው ፡ በእውነተኞች ፡ ምስክሮች ፡ ከተረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ ገንዘባቸውን ፡ ሁሉ ፡ ሊከፍላቸው ፡ ይገባዋል ። አምላካዊ ፡ ከሆነ ፡ ዕዳ ፡ ወገን ፡ በመዋቲ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ይህን ፡ የሚከተል ፡ ነው ። ይኸውም ፡ እንደ ፡ ብፅአት ፡ ያለ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሕጉን ፡ ትእዛዝ ፡ ያድርጉ

፩ሺ፫፻፲፬ እነሆ ፡ ስለ ፡ አዛዥም ፡ ከገንዘቡ ፡ ከእኩሌታውና ፡ ከአራተኛው ፡ እጅ ፡ በገንዘቡ ፡ ትእዛዝ ፡ ያዝዝ ፡ ዘንድ ፡ እንዳይገባው ፡ አስቀድመን ፡ ተናግረናል ። አራተኛው ፡ እጅ ፡ ሊወርስ ፡ ለሚገባው ፡ ሰው ፡ ይቅር ። በዚህ ፡ ማዘዝ ፡ የለም ።

፩ሺ፫፻፲፭ ጠሰ ፡ ፴፩ ። ፴፯ ። የሟቹን ፡ ወራሾች ፡ ወይም ፡ ቤተ ፡ ሰቦቹን ፡ ወይም ፡ ዋሶችን ፡ አዘንተኞች ፡ ከሚሆኑባቸው ፡ ከ፱ ፡ ቀኖች ፡ ፍጻሜ ፡ አስቀድሞ ፡ ሊይዛቸው ፡ ወይም ፡ ከሥራ ፡ በማናቸውም ፡ ሥራ ፡ ሊያሳዝናቸው ፡ ወይም ፡ በሟቹ ፡ ላይ ፡ ባለ ፡ ብድርና ፡ ዕዳ ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ሸንጎ ፡ ሊወስዳቸው ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ምክንያት ፡ ሊይዛቸው ፡ ለማንም ፡ አይገባውም ።

፩ሺ፫፻፲፮ ዘጠኙን ፡ ቀን ፡ ከመፈጸማቸው ፡ አስቀድሞ ፡ አንዱ ፡ ተደፋፍሮ ፡ ከእነርሱ ፡ አንዱን ፡ ቢይዘው ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ገንዘቡን ፡ በመያዝ ፡ ወይም ፡ በዋስነቱ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ኀይል ፡ ቢያደርግ ፡ ይህ ፡ ፈራሽ ፡ ነው ። የተወሰነችው ፡ ቀን ፡ ከተፈጸመች ፡ ግን ፡ በሕግ ፡ በሚገባ ፡ እንግዲህ ፡ ሊከራከሩ ፡ ይገባል ።

፩ሺ፫፻፲፯ ሁለተኛው ፡ ምዕራፍ ። ያወራረስን ፡ ትእዛዝና ፡ የወራሾችንም ፡ የመዓርግ ፡ ሥርዓት ፡ ስለሚያስረዳ ፡ ስለመጨረሻው ፡ ነገር ፡ ይናገራል ። አወራረስ ፡ ከሁለት ፡ ይከፈላል ። ከእነ

አንቀጽ ፡ ፵፪ ።

ሎቱ ፡ ትእዛዝ ፡ በክፍል ፡ እሙራ ፡ ምስለ ፡ ወራ
ስያን ። ወኵልቄ ፡ ትእዛዛትኒ ፡ እምኔሁ ፡ ፮ቱ ።

፩ሺ፫፻፲፰ ለብእሲት ፡ ይደልዋ ፡ ላቲ ፡ ምስለ ፡ ወራስያኒሁ
ለምታ ፡ መንፈቀ ፡ ንዋይ ፡ ለእመ ፡ ኢኮኑ ፡
ውሉዳ ፡ በተዓርዮታ ፡ ምስለ ፡ ፩ዱ ፡ እምው
ሉድ ፡ ወበዕሪና ፡ ይንሥኡ ፡ ደቂቅ ፡ ወከማሁ ፡
ለብእሲኒ ፡ ምስለ ፡ ብእሲቱ ፡ ዝንቱ ፡ እማሬ ።

፩ሺ፫፻፲፱ ለአኃው ፡ ምዉት ፡ ሎሙ ፡ ምስለ ፡ እሙ ፡
ሣልስተ ፡ እድ ፡ ወግብረ ፡ ደቂቆሙ ፡ እምድኅ
ሬሆሙ ፡ ምስሌሃ ፡ ኅቡረ ። ከማሁ ፡ እምኔዉ ፡
ለዘሞተ ወእምዝ ፡ እምኔውቱ ፡ ዘእቡሁ ፡
ላቲ ፡ ምስለ ፡ አኃዊሁ ፡ ወአኃቲሁ ፡ ሣልስተ ፡
እድ ።

፩ሺ፫፻፳ ወካልእኒ ፡ ክፍል ፡ ረስዩ ፡ ሎሙ ፡ ነሚአ ፡
ርስት ፡ ለአዝማድ ፡ ወለነገደ ፡ እብ ፡ ለእደው ፡
ወለአንስት ፡ እምቅድመ ፡ አዝማደ እም ።
ወኵልቆሙሰ ፡ ይኩን ፡ በከመ ፡ ተሰነአዉ ፡
ቦቱ ፡ ቀኖናት ፡ ዘነገሥት ፡ ወፍጻሜ ፡ እማሬ ።
ወኢሀሎ ፡ ዘኢተዘከረ ፡ በቀኖናት ፡ በከመ ፡
ዘከሩ ፡ በውስቴቶን ፡ ፳ወ፪ቱ ፡ መዓርጋት ።

፩ሺ፫፻፳፩ መዓርግ ፡ ቀዳማዊ ፡ ውሉዱ ፡ ለምዉት ፡
እደው ፡ ወአንስት ፡ በዕሩይ ። ወዳግማዊ ፡
እደው ፡ ወአንስት ፡ በዕሩይ ፡ ለውሉደ ፡ ውሉድ
ተባዕት ፡ በበመዓርጊሆሙ ፡ መዓርግ ፡ ድኅረ ፡
መዓርግ ። ወሣልስ ፡ እብ ።

፩ሺ፫፻፳፪ ወራብዕ ፡ ለፍጹማን ፡ አኃወ ፡ ምውት ፡ ወአ
ኃቲሁ ፡ ወእሙ ፡ በዕሩይ ። ወኃምስ ፡ አኃው ፡
ወአኃት ፡ እለ ፡ እምአብ ፡ ባሕቲቱ ። ወሳድስ ፡
አኃው ፡ ወአኃት ፡ እለ ፡ እምእም ፡ ባሕቲታ ።

፩ሺ፫፻፳፫ ወሳብዕ ፡ ተባዕት ፡ ወአንስት ፡ እምውሉደ ፡
አኃዊሁ ፡ ለዘሞተ ፡ በዕሩይ ። ወሳምን ፡ ተባ
ዕት ፡ ወአንስት ፡ እምውሉደ ፡ ውሉዶሙ ፡ ተባ
ዕት ፡ በበመዓርጊሆሙ ፡ መዓርግ ፡ ድኅረ ፡ መዓ
ርግ ።

፩ሺ፫፻፳፬ ወታስዕ ፡ እበ ፡ እቡሁ ፡ ለዘሞተ ። ወዓሥር ፡
እመ ፡ እቡሁ ።

፩ሺ፫፻፳፭ ፲ወ፩ዱ ፡ እኁወ ፡ እብ ። ፲ወ፪ቱ ፡ተባዕት ፡

ስለ ፡ ርስት ።

ርሱ ፡ አንዱ ፡ በታወቀው ፡ ክፍል ፡ ከወራሾች ፡
ጋር ፡ ትእዛዝ ፡ ለታዘዘለት ፡ ነው ። ከእርሱም ፡
የትእዛዛቱ ፡ ቍጥር ፡ ፮ ፡ ነው ።

፩ሺ፫፻፲፰ ሚስት ፡ ልጇ ፡ካልሆኑ ፡ ከባሏ ፡ ወራሾች ፡
ጋር ፡ የገንዘብ ፡ እኩሌታ ፡ ይገባታል ። ልጇ ፡
ቢሆኑ ፡ ግን ፡ ከልጆች ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ በት
ክክል ፡ ነው ። ልጆቹም ፡ በትክክል ፡ ይውሰዱ ።
እንደዚሁም ፡ ለባል ፡ ከሚስቱ ፡ ጋራ ፡ ይህ ፡
አስተያየት ፡ ነው ።

፩ሺ፫፻፲፱ ለሟች ፡ ወንድሞችም ፡ ከእናቱ ፡ ጋራ ፡ ፫ ፡
እጅ ፡ ይገባቸዋል ። ከእነርሱም ፡ በኋላ ፡ ከእ
ርሷ ፡ ጋራ ፡ በአንድነት ፡ የልጆች ፡ ግብር ፡
(አወራረስ፡) ነው ። የሟች ፡ ወንድ ፡ አያቱም ፡
እንደዚሁ ፡ ነው ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በአባቱ ፡
በኩል ፡ ሴት ፡ አያቱ ፡ ከወንድሞቹና ፡ ከእኅ
ቶቹ ፡ ጋር ፡ ፫ ፡ እጅ ፡ ይገባታል ።

፩ሺ፫፻፳ ፪ኛውም ፡ ክፍል ፡ ርስት ፡ መቀበልን ፡ ከእ
ናት ፡ ዘመዶች ፡ አስቀድሞ ፡ ለአባት ፡ ዘመዶ
ችና ፡ ወገኖች ፡ ለወንዶችና ፡ ለሴቶችም ፡ አደ
ረጉ ። ቍጥራቸው ፡ ግን ፡ የነገሥታት ፡ መጻሕ
ፍት ፡ እንደተስማሙበት ፡ ይሁን ። የማመል
ከቱ ፡ መጨረሻ ፡ ኻያ ፡ ሁለቱን ፡ መዓርጋት ፡
በውስጣቸው ፡ እንደተናገሩ ፡ መጠን ፡ በመጻሕ
ፍት ፡ ያልተነገረ ፡ የለም ።

፩ሺ፫፻፳፩ መጀመሪያ ፡ መዓርግ ፡ የሙት ፡ ልጆች ፡ ወን
ዶችና ፡ ሴቶች ፡ በትክክል ፡ ይውረሱ ። ሁለተኛ
ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ በትክክል ። ለወንዶች ፡
የልጅ ፡ ልጆች ፡ በየመዓርጋቸው ። ከመዓርግ ፡
ቀጥሎ ፡ መዓርግ ።

፩ሺ፫፻፳፪ ሦስተኛ ፡ አባት ፡ ነው ። አራተኛ ፡ የሟቹ ፡
ፍጹማን ፡ የሆኑ ፡ ወንድሞቹና ፡ እኅቶቹ ፡ እና
ቱም ፡ በትክክል ፡ ይካፈሉ ። አምስተኛ ፡ ከአ
ባት ፡ ብቻ ፡ የሚወለዱ ፡ ወንድሞችና ፡ እኅ
ቶች ። ስድስተኛ ፡ ከእናት ፡ ብቻ ፡ የሚወለዱ ፡
ወንድሞችና ፡ እኅቶች ።

፩ሺ፫፻፳፫ ሰባተኛ ፡ ከሟቹ ፡ ከወንድሞቹ ፡ ልጆች ፡ ወን
ዶችና ፡ ሴቶች ፡ በትክክል ፡ ይካፈሉ ። ስምንተ
ኛ ፡ ከወንዶች ፡ የልጆቻቸው ፡ ልጆች ፡ ወንዶ
ችና ፡ ሴቶች ፡ በየመዓርጋቸው ፡ ከመዓርግ ፡
ቀጥሎ ፡ መዓርግ ።

፩ሺ፫፻፳፬ ዘጠኝኛ ፡ የሟቹ ፡ ያባቱ ፡ አባት ፡ (አያቱ) ፡
አሥረኛ ፡ የአባቱ ፡ እናት ፡ (ሴት ፡ አያቱ) ።

፩ሺ፫፻፳፭ ፲፩ኛ ፡ ያባት ፡ ወንድሞች ፡ ፲፪ተኛ ፡ ከአባት ፡

አንቀጽ ፡ ፵፪ ።

ወእኅስት ፡ እምውሉዶ ፡ እኁወ ፡ አብ ፡ በዕሩይ ፡ በበመዓርጊሆሙ ፡ መዓርግ ፡ ድኅረ ፡ መዓርግ ።

፩ሺ፫፻፹፮ ፲ወ፫ቱ ፡ ተባዕት ፡ ወእንስት ፡ እምውሉዶ ፡ አዋልዲሁ ፡ ለዘሞተ ፡ በዕሩይ ፡ በበመዓርጊሆሙ ፡ መዓርግ ፡ ድኅረ ፡ መዓርግ ። ፲ወ፬ቱ ፡ ተባዕት ፡ ወእንስት ፡ እምውሉዶ ፡ አኀዊሁ ፡ ለመዋቲ ፡ በዕሩይ ፡ በበመዓርጊሆሙ ፡ መዓርግ ድኅረ ፡ መዓርግ ። ፲ወ፭ቱ ፡ ተባዕት ፡ ወእንስት ፡ እምውሉደ ፡ ውሉደ ፡ እኅቱሁ ፡ በዕሩይ ፡ በበመዓርጊሆሙ ፡ መዓርግ ፡ ድኅረ ፡ መዓርግ ።

፩ሺ፫፻፹፯ ፲ወ፮ቱ ፡ ተባዕት ፡ ወእንስት ፡ እምውሉዶ ፡ ውሉዶሙ ፡ ለእኁወ ፡ አቡሁ ፡ በበመዓርጊሆሙ ፡ መዓርግ ፡ ድኅረ ፡ መዓርግ ።

፩ሺ፫፻፹፰ ፲ወ፯ቱ ፡ እኅተ ፡ አቡሁ ፡ ለዘሞተ ፡ ወውሉዶን ፡ ተባዕት ፡ ወእንስት ፡ በዕሩይ ፡ በበመዓርጊሆሙ ፡ መዓርግ ፡ ድኅረ ፡ መዓርግ ።

፩ሺ፫፻፹፱ ፲ወ፰ቱ ፡ አብ ፡ እሙ ፡ ለዘሞተ ። ፲ወ፱ቱ ፡ እማ ፡ ለእሙ ።

፩ሺ፫፻፺ ፳ ፡ እኁወ ፡ እሙ ፡ ለዘሞተ ፡ ተባዕት ፡ ወእንስት ፡ እምውሉዶሙ ፡ በዕሩይ ፡ በበመዓርጎሙ ፡ መዓርግ ፡ እምድኅረ ፡ መዓርግ ። ፳ወ፩ዱ ፡ እኅተ ፡ እሙ ፡ ለዘሞተ ፡ ተባዕት ፡ ወእንስት ፡ እምውሉዶሙ ፡ በዕሩይ ፡ በበመዓርጊሆሙ ፡ መዓርግ ፡ እምድኅረ ፡ መዓርግ ።

፩ሺ፫፻፺፩ ፳ወ፪ቱ ፡ አበወ ፡ እምኔዋን ፡ ወእምድኅሬሆሙ ፡ ቅሩባን ፡ አዝማድ ፡ ወርኁቃን ፡ አዝማድ ፡ እስመ ፡ ተዋርሶ ፡ ሥሩዕ ፡ ከመ ፡ ይረሱ፡ ቅሩባን ፡ አዝማድ ፡ ወርኁቃን ፡ አዝማድ ።

፩ሺ፫፻፺፪ ወአቅድሙ ፡ መዓርገ ፡ ውሉዱ ፡ ለዘሞተ ፡ ወውሉዶሙ ፡ እመዓርገ ፡ አቡሁ ። ወዓዲ ፡ አቅድሙ ፡ ዘመደ ፡ አብ ፡ እምአዝማደ ፡ እም ፡ ወከመ ፡ ይረሱ ፡ ተባዕት ፡ እምቅድመ ፡ እንስት ፡ በውስተ ፡ መዓርገ ፡ እኁወ ፡ አብ ፡ ወእኁወ ፡ እም ፡ ወእምኔሆሙ ። ወከመ ፡ ይትዐረዩ ፡ እለ ፡ ገብራን ፡ ተባዕት ፡ ወእንስት ፡ ወይረሱ ፡ እለ ፡ ፍጹማን ፡ እምእኁው ፡ እምቅድመ ፡ እለ ፡ ኢኮኑ ፡ ፍጹማነ ።

፩ሺ፫፻፺፫ ወኵሉ ፡ መዓርግ ፡ እምነ ፡ እሉ ፡ መዓርጋት ፡ እለ ፡ እሙራት ፡ ወሥሩዓት ፡ ዘአቅደምነ ፡ ዘከሮቶሙ ፡ ከመ ፡ ኢይረስ ፡ ዕዱሂ ፡ ምስሌሆሙ ፡ እምእለ ፡ ይዜክርዎሙ ፡ ድኅረ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘዐ

ስለ ፡ ርስት ።

ወንድሞች ፡ ልጆች ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ በትክክል ፡ በየመዓርጋቸው ። ከመዓርግ ፡ ቀጥሎ ፡ መዓርግ ።

፩ሺ፫፻፹፮ ፲፫ተኛ ፡ ከሟቹ ፡ የሴቶች ፡ ልጆቹ ፡ ልጆች ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ በትክክል ፡ በየመዓርጋቸው ። ከመዓርግ ፡ ቀጥሎ ፡ መዓርግ ። ፲፬ተኛ ፡ ከሟቹ ፡ የእኅቶቹ ፡ ልጆች ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶችም ፡ በትክክል ፡ በየመዓርጋቸው ። ከመዓርግ ፡ ቀጥሎ ፡ መዓርግ ። ፲፭ተኛ ፡ ከእኅቶቹ ፡ የልጅ ፡ ልጆች ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ በትክክል ፡ በየመዓርጋቸው ፡ ከመዓርግ ፡ ቀጥሎ ፡ መዓርግ ።

፩ሺ፫፻፹፯ ፲፮ተኛ ፡ ከአባቱ ፡ ወንድሞች ፡ የልጅ ፡ ልጆች ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ በየመዓርጋቸው ፡ ከመዓርግ ፡ ቀጥሎ ፡ መዓርግ ።

፩ሺ፫፻፹፰ ፲፯ተኛ ፡ የሟቹ ፡ የአባቱ ፡ እኅቶች ፡ ልጆቻቸውም ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ በትክክል ፡ በየመዓርጋቸው ። ከመዓርግ ፡ ቀጥሎ ፡ መዓርግ።

፩ሺ፫፻፹፱ ፲፰ተኛ ፡ የሟች ፡ የእናቱ ፡ አባት ፡ ፲፱ኛ ፡ የእናቱ ፡ እናት ።

፩ሺ፫፻፺ ፳ኛ ፡ የሟች ፡ የእናቱ ፡ ወንድሞች ፡ ከልጆቻቸው ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ በትክክል ፡ በየመዓርጋቸው ፡ ከመዓርግ ፡ ቀጥሎ ፡ መዓርግ ። ፳፩ኛ ፡ የሟች ፡ የእናቱ ፡ እኅቶች ፡ ከልጆቻቸው ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ በትክክል ፡ በየመዓርጋቸው ። ከመዓርግ ፡ ቀጥሎ ፡ መዓርግ ።

፩ሺ፫፻፺፩ ፳፪ኛ ፡ ያያቶች ፡ አባቶች ፡ (ቀድመ ፡ አያቶች) ፡ ከእነርሱም ፡ በኋላ ፡ የቅርብ ፡ ዘመዶችና ፡ የሩቅ ፡ ዘመዶች ። የቅርብ ፡ ዘመዶችና ፡ የሩቅ ፡ ዘመዶች ፡ እንዲወርሱ ፡ አወራረስ ፡ ታዝዟልና ።

፩ሺ፫፻፺፪ የሟችን ፡ የልጆቹንና ፡ የልጆቻቸውን ፡ መዓርግ ፡ ከአባት ፡ መዓርግ ፡ አስቀድሙ ። ዳግመኛም ፡ ከእናት ፡ ዘመዶች ፡ የአባትን ፡ ዘመዶች ፡ አስቀድሙ ። በአባት ፡ ወንድሞችና ፡ በእናት ፡ ወንድሞች ፡ በእያትም ፡ መዓርግ ፡ ወንዶች ፡ ከሴቶች ፡ ቀድመው ፡ ይወርሱ ፡ ዘንድ ፡ የተጠቀሱትም ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ይተካከሉ ፡ ዘንድ ፡ ፍጹማን ካልሆኑት ፡ አስቀድመው ፡ ከወንድሞች ፡ ፍጹማን ፡ የሆኑት ፡ ይውረሱ ።

፩ሺ፫፻፺፫ ነገራቸውን ፡ ካስቀደምነው ፡ ከታዘዙትና ፡ ከታወቁት ፡ መዓርጋት ፡ ወገን ፡ መዓርግ ፡ ሁሉ፡ ኋላ ፡ ከሚናገራቸው ፡ አንዱስ ፡ አንኳ ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ እንዳይወርስ ። ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ትእ

ለዎ ፡ ትእዛዘ ፡ ምስሌሆሙ ። ወእመቦ ፡ ዘተፈልጠ ፡ እምኒ ፡ እሉ ፡ ወራስያን ፡ ይረስ ፡ ኵሎ ፡ ንዋዮ ፡ ለዘአውረሰ ፡ ኵለንታሁ ። ወእመ ተኀበረ ፡ ምስለ ፡ እሉ ፡ ትእዛዝ ፡ ይንሣእ ፡ ዘተርፈ ፡ እምድኅረ ፡ ትእዛዝ ።

፩ሺ፫፻፴፬ ምዕራፍ ፫ቱ ። በእንተ ፡ ዘይወርስ ፡ ብእሲ ፡ እምብእሲቱ ፡ ወብእሲት ፡ እምብእሲሃ ። ወምክንያተ ፡ ቀዳምስ ፡ ዘከነ ፡ ለብእሲ ፡ ወብእሲት በውስተ ፡ ርስት ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ይከውኑ ፡ ጥንተ ፡ ለካልአኒሆሙ ፡ በተሳትፎቶሙ ፡ በሕገ ተዋስቦ ። እስመ ፡ በተዋስቦ ፡ ይትዋለዱ ፡ ውሉድ ፡ ወይሰመዩ ፡ ወላድያን ፡ አበው ፡ ወበተዋስቦ ፡ ይከውኑ ፡ ፩ደ ፡ ሥጋ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወለ፩ዱ ፡ እምእሉ ፡ ይደልዎ ፡ ንዋዮ ፡ ካልኡ ።

፩ሺ፫፻፴፭ ሥርዋጽ ፡ ይትዐወቅ ፡ ከመ ፡ አ ፡ እምአበው ወአ ፡ እምኀዋት ፡ ወአ ፡ እምውሉድ ፡ ወውሉዶሙ ፡ ወአ ፡ እምአኀው ፡ ወአኀው ፡ አብ ፡ ወአኀወ ፡ እም ፡ ወውሉዶ ፡ ዝኩራን ።

፩ሺ፫፻፴፮ ወስ ፡ ፴ ፡ ወለእመ ፡ ሞተ ፡ ብእሲ ፡ አው ፡ ብእሲት ፡ ዘእንበለ ፡ የአዝዙ ፡ ኑዛዜሆሙ ፡ ወኢ ልቦሙ ፡ ወራሲ ፡ ወባዕዓዊ ፡ አ ፡ እምኒ ፡ ዘይትሌዓሉ ፡ ወአ ፡ እምኒ ፡ ዘይቴሕቱ ፡ ወአ ፡ እምኀበዋት ፡ እስመ ፡ ብእሲ ፡ አሚሃ ፡ ይቀውም ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ርስተ ፡ ብእሲቱ ፡ ወከማሁ ፡ ይደሉ ፡ ብእሲትኒ ፡ ትቁም ፡ ላዕለ ፡ ርስተ ፡ ምታ ።

፩ሺ፫፻፴፯ ወበፍጻሜ ፡ ኀብኤሁ ፡ ይቤ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ገብርኤል ፡ ለእመ ፡ ቦቱ ፡ ብእሲት ፡ ወላቲ ፡ ውሉድ ፡ ትትኌለቍ ፡ ከመ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ዲድስቅልያ ፡ ሀቡ ፡ ለድኩታማን ፡ ንዋየ ፡ አበዊሆሙ ፡ ወለመበለታት ፡ ንዋየ ፡ እምታቲሆን ። ወዝንቱ ፡ ቃል ፡ ይነግር ፡ ከመ ፡ የሀቡ ፡ ርስቶ ፡ ለዘሞተ ፡ ለውሉዱ ፡ ወለብእሲቱ ። ወለእመ ፡ ኢፈለጠ ፡ ከመ፡ የሀቡ ፡ ለለ፩ዱ ፡ በስሙ ፡ ወኵሎሙ ፡ ስሩያን ፡ ይኩኑ ።

፩ሺ፫፻፴፰ ወዳግሚ ፡ ለማድ ፡ ለእመ ፡ ሞተ ፡ ፩ዱ ፡ እምክልኤሆሙ ፡ ውስተ ፡ ውሳኔ ፡ ወራስያን ፡ ካልአን ፡ ዘእንበለ ፡ ብእሲቱ ፡ እንዘ ፡ አልቦቱ ፡ ውሉድ ፡ ወራስያን ፡ ይኩን ፡ መንፈቀ ፡ ንዋዩ ፡ ዘኀደገ ፡ ለብእሲቱ ፡ ወካልእ ፡ መንፈቅ ፡ ለእለ፡



ዛዝ ፡ ያለው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ። ከእነዚህ ፡ ወራሾች ፡ የተለየ ፡ ቢኖር ፡ ያውራሹን ፡ መላውን ፡ ገንዘብ ፡ ይውረስ ። ከእነዚህ ፡ ጋራ ፡ ትእዛዝ ፡ ቢተባበር ፡ ከትእዛዝ ፡ በኋላ ፡ የቀረውን ፡ ይውሰድ ።

፩ሺ፫፻፴፬ ሦስተኛው ፡ ምዕራፍ ። ባል ፡ ከሚስቱ ፡ ስለሚወርስ ፡ ሴትም ፡ ከባሏ ፡ ስለምትወርስ ፡ ይናገራል ። በአወራረስ ፡ ጊዜ ፡ ለባልና ፡ ሚስት ፡ የሆነው ፡ የመቅደም ፡ ምክንያትስ ፡ እነርሱ ፡ በጋብቻ ፡ ሥርዓት ፡ አንድ ፡ በመሆናቸው ፡ ለሌሎች ፡ ጥንት ፡ ስለሚሆኑ ፡ ነው ። በጋብቻ ፡ ልጆች ፡ ይወለዳሉ ፡ ወላጆችም ፡ አባቶች ፡ ይባላሉና ። እግዚአብሔርም ፡ እንደተናገረ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ይሆናሉ ። (ዘፍ ፡ ፪ ፡ ፳፬) ፡ ከእሊህ ፡ ለአንዱ ፡ የሌላው ፡ ገንዘብ ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ፫፻፴፭ ሥርዋጽ ። ከአባቶችና ፡ እያቶች ፡ ከልጆችና፡ ከልጆቻቸው ፡ ከወንድሞችና ፡ ከአባት ፡ ወንድሞች ፡ ከእናትም ፡ ወንድሞች ፡ ከተጠሩትም ፡ ልጆች ፡ እንዳልሆነ ፡ ይታወቃል ።

፩ሺ፫፻፴፮ ጠስ ፡ ፴ ። ባል ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ ቋፈው ፡ ሳያዝዙ ፡ ቢሞቱ ፡ ወራሽ ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ ባይኖራቸው ፡ ወደላይ ፡ ካሉም ፡ ቢሆን ፡ (እናት ፡ አባት ፡ አያት) ፡ ወደታች ፡ ካሉም ፡ ቢሆን ፡ (ልጅ ፡ የልጅ ፡ ልጅ) ፡ ወደጎን ፡ ካሉም፡ ቢሆን ፡ (እኅት ፡ ወንድም) ፡ ባል ፡ ነውና ፡ ያን ጊዜ ፡ በሚስቱ ፡ ርስት ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ይተካል ። እንደዚሁም ፡ ሚስት ፡ በባሏ ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ ትተካ ።

፩ሺ፫፻፴፯ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ገብርኤል ፡ በመጽሐፉ ፡ መጨረሻ ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ሚስት ፡ ብትኖረው፡ ልጆችም ፡ ቢኖሯት ፡ ከእነርሱ ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ትቈጠር ፡ ብሏል ። ዲድስቅልያ ፡ ለድኆ ፡ አደጎች ፡ ያባቶቻቸውን ፡ ገንዘብ ፡ ባሎቻቸው ፡ ለሞቱባቸውም ፡ የባሎቻቸውን ፡ ገንዘብ ፡ ስጡ ፡ እንዳለ ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ የሟችን ፡ ርስት ፡ ለልጆቹና ፡ ለሚስቱ ፡ እንዲሰጡ ፡ ይናገራል ። ለያንዳንዱ ፡ ይሰጡ ፡ ዘንድ ፡ ስሙን ፡ ባይለይ ፡ ሁሉም ፡ ትክክል ፡ ይሁኑ ።

፩ሺ፫፻፴፰ ዳግመኛም ፡ ለማድ ፡ አለ ። ከሁለቱ ፡ ከባልና ፡ ከሚስት ፡ አንዱ ፡ ቢሞት ፡ ከሚስቱ ፡ በቀር ፡ ሌሎች ፡ ወራሾችን ፡ ቢተው ፡ የሚወርሱ ፡ ልጆች ፡ ሳይኖሩት ፡ የተወው ፡ የገንዘቡ ፡ እኩሌታ ፡ ለሚስቱ ፡ ይሁን ። ሁለተኛው ፡ እኩ

አንቀጽ ፡ ፵፪ ።

ይደልዎሙ ፡ ይረስዎ ፡ ለዘሞተ ፡ ወዝንቱ ፡ የነ ብር ፡ ካዕበ ፡ ምስለ ፡ ዘተነግረ ።

፩ሺ፫፻፶፱ መክ ፡ ፶ወ፩ዱ ፡ ወለእለ ፡ የሐፅዩ ፡ እመቦ ፡ ብእሲ ፡ ዘሐፀየ ፡ ብእሲተ ፡ ወሞተ ፡ ዘእንበለ ፡ ያውስባ ፡ ይኩን ፡ ላቲ ፡ መንፈቀ ፡ ንዋይ ፡ ዘወሀባ ፡ ወለእዝማዲሁ ፡ መንፈቅ ።

፩ሺ፫፻፷ ወለእመሰ ፡ አልቦቱ ፡ ወራሲ ፡ ዘእንበሌሃ ፡ ይኩን ፡ ላቲ ፡ ኵሉ ንዋዩ ። ወበፍጻሜ ፡ ኀበ ፡ ኢሁ ፡ ካልእ ፡ ይቤ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ገብር ኤል ፡ ዝንቱ ፡ ኵሉ ፡ ፍትሕ ፡ ወአምሳል ፡ ይትፌጸም ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ሥርዓተ ፡ ፩ዱ ፡ እምኒሆሙ ፡ በከመ ፡ ሥርዓተ ፡ ካልኡ ፡ ሎቱ ፡ በከመ ይቤሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለብእሲ ፡ ንግበር ፡ ሎቱ ፡ ቢጸ ፡ ዘይረድኦ ፡ ወበብዝሎቱ ፡ ዓዲ ፡ ከመ ፡ እሙንቱ ፡ ይከውኑ ፡ ፩ደ ፡ ሥጋ ፡ ወእኮ ፡ ፪ተ ። ወይኩንኬ ፡ ለብእሲ ፡ እምነ ፡ ብእሲቱ ፡ በከመ ፡ ተሠርዐ ፡ ላቲ ፡ እምኔሁ ፡ መንፈቀ ፡ ንዋዩ ፡ ምስለ ፡ እዝማዲሁ ፡ ካልእን ፡ ዘእን በለ ፡ ውሉዱ ፡ ወሰሪና ፡ ለለ፩ዱ ፡ እምውሉዱ ፡ ወክሎሙ ፡ ምስለ ፡ ተካፍሎቱ ፡ ኵሎሙ ።

፩ሺ፫፻፷፩ ወለእመሰ ፡ ማእከለ ፡ ብእሲ ፡ ወብእሲቱ ፡ ሀሎ ፡ ግብረ ፡ ተዘምዶ ፡ ይኩን ፡ ሥርዓተ ፡ ምጣኔ ፡ ከመ ፡ ይረስ ፡ ኵሉ ፡ ለለ፩ዱ ፡ እምካልኡ ፡ ፪ተ ፡ ክፍለ ፡ ፩ዱ ፡ ዘተዋስቦ ፡ ወካልኡ ፡ ዘተዘምዶ ።

፩ሺ፫፻፷፪ ወበምሰራፍ ፡ ዘሕገ ፡ ተዋስቦ ፡ ሀሎ ፡ ቀኖና ፡ ካልእ ። ወውእቱ ፡ መክ ፡ ፶ወ፩ዱ ፡ ወእመ ፡ ሞተ ፡ ምታ ፡ ይኩን ፡ ላቲ ፡ ኵሉ ፡ ትሎታ ፡ ወመንፈቀ ፡ ሕፄሃ ፡ ወእመኒ ፡ ሞተት ፡ ብእሲቱ ፡ ወተርፈ ፡ ምታ ፡ ወባቲ ፡ ለብእሲት ፡ ውሉድ ፡ እምኔሁ ፡ አው ፡ እመ ፡ እልባቲ ፡ ይኩን ፡ ሎቱ ፡ ኵሉ ፡ ሕፄሃ ፡ ወመንፈቀ ፡ ትል ወታ ፡ ዘእምጽአት ፡ ኀቤሁ ።

፩ሺ፫፻፷፫ ዘ፹ወ፱ቱ ፡ ወለእመኒ ፡ ሞተ ፡ ብእሲ ፡ ወአል ባቲ ፡ ለብእሲቱ ፡ ወልድ ፡ እምኔሁ ፡ ይኩን ፡ ላቲ ፡ ትልወታ ፡ ወመንፈቀ ፡ ሕፄሃ ። እመሰ ፡ ትልወታ ፡ በልየ ፡ ወኀልቀ ፡ ይደልዋ ፡ ላቲ ፡ ሤጠ ፡ እሉ ፡ አልባስ ፡ ዘእምጽእቶሙ ፡ ምስ ሌሃ ፡ በከመ ፡ ጊዜ ፡ ዘቦቱ ፡ መጽአት ፡ ለቢሳ ፡ ኪያሆሙ ። ወለእመ ፡ ኢተርፈ ፡ እምኔሁ ፡ ይት

ስለ ፡ ርስት ።

ሌታ ፡ ሚቴን ፡ ሊወርሱት ፡ ለሚገባቸው ፡ ሰዎች ፡ ይሁን ። ይህ ፡ ዳግመኛ ፡ ከተነገረው ፡ ጋር ፡ ይተባበራል ።

፩ሺ፫፻፶፱ መክ ፡ ፶፩ ። ለሚያጩ ፡ ሰዎች ፡ ሚስት ፡ ያጨ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ሳያገባትም ፡ ቢሞት ፡ ከሰጣት ፡ ገንዘብ ፡ እኩሌታው ፡ ለእርሷ ፡ እኩሌታውም ፡ ለዘመዶቹ ፡ ይሁን ። ያለ ፡ እርሷ ፡ ወራሽ ፡ ባይኖረው ፡ ግን ፡ መላው ፡ ለእርሷ ፡ ይሁን ።

፩ሺ፫፻፷ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ገብርኤል ፡ በሁለተኛው፡ መጽሐፉ ፡ መጨረሻ ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ፍርድና ፡ ምሳሌ ፡ ከእነሱ ፡ ያንዱ ፡ ሥር ዓት ፡ እንደ ፡ ሁለተኛው ፡ ሥርዓት ፡ እንዲሆን፡ ይፈጸማል ። እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ የምትረ ዳው ፡ ጓደኛ ፡ እንፍጠርለት ፡ እንዳለው ፡ ዳግ መኛም ፡ እነርሱ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ እንደሚሆኑ ፡ ሁለትም ፡ እንዳይደሉ ፡ በማለቱ ።(ዘፍ ፡ ፪፣፲፰) ያለ ፡ ልጆቹ ፡ ከሌሎች ፡ ዘመዶቹ ፡ ጋራ ፡ የገን ዘቡ ፡ እኩሌታ ፡ ከእርሱ ፡ ለእርስዋ ፡ እንደታ ዘዘ ፡ ለባልም ፡ ከሚስቱ ፡ ገንዘብ ፡ ይሁን ። ከልጆቹም ፡ ለእያንዳንዱ ፡ መተካከል ፡ ይገ ባል ። ሁለም ፡ ከታጡ ፡ ሁሉን ፡ ይውረስ ።

፩ሺ፫፻፷፩ በባልና ፡ በሚስት ፡ መካከል ፡ የዝምድና ፡ ሥርዓት ፡ ቢኖር ፡ ሁሉም ፡ እያንዳንዱ ፡ ከሌ ላው ፡ ሁለት ፡ ዕጣ ፡ ይወርስ ፡ ዘንድ ፡ ልክ ፡ ያለው ፡ ሥርዓት ፡ ይሁን ። አንዱ ፡ የጋብቻ ፡ አንዱ ፡ የተዘምዶ ፡ ነው ።

፩ሺ፫፻፷፪ በጋብቻ ፡ ሥርዓት ፡ ምሰራፍ ፡ ሌላ ፡ ትእዛዝ ፡ አለ ። ይኸውም ፡ መክ ፡ ፶፩ ። ባልዋ ፡ ቢሞት ፡ ትልወቷ ፡ ሁሉና ፡ የማጫዋ ፡ እኩሌታ ፡ ለእርሷ ይሁን ። ሚስቱም ፡ ሞታ ፡ ባልዋ ፡ ቢቀር ፡ ለሚስቱ ፡ ከእርሱ ፡ ልጆች ፡ ቢኖሯት ፡ ወይም ፡ ባይኖሯት ፡ ማጫዋ ፡ ሁሉና ፡ ወደእርሱ ፡ ይዛው የመጣችው ፡ የትልወቷ ፡ እኩሌታ ፡ ለእርሱ ፡ ይሁን ።

፩ሺ፫፻፷፫ ፹፱ ። ባል ፡ ቢሞት ፡ ለሚስቱ ፡ ከእርሱ ፡ ልጅ ባይኖራት ፡ ትልወቷና ፡ የማጫዋ ፡ እኩሌታ ፡ ለእርሷ ፡ ይሁን ። ትልወቷ ። ቢያረጅና ፡ ቢያ ልቅ ፡ ለብሳቸው ፡ እንደመጣችበት ፡ ጊዜ ፡ ከእ ርሷ ፡ ጋራ ፡ ያመጣቻቸው ፡ የእሊያ ፡ ልብሶች ፡ ዋጋ ፡ ለእርሷ ፡ ይገባታል ። ከእርሱ ፡ ባይቀር ፡ የዋ ጋውን ፡ ልክ ፡ የሚያመለክት ፡ ይብዳቢ ፡ ይታይ ።

ረእዩ ፡ ክታብ ፡ ዘይኤምር ፡ ምግኔ ፡ ሜጠ ፡ ዚአሁ ፡ ይትዐወቅ ፡ ሜጡ ፡ እመጽሐፍ ፡ እንተ፡ ይከውን ፡ ማእከሌሆሙ ፡ ወዘወደይዎ ፡ በኅ ብር ፡ ዘሰጡቅ ፡ ሜጡ ፡ ወከማሁ ፡ ካልእንሂ ፡ ዘአምጽእት ።

፩ሺ፫፻፺፪ ወለእመ ፡ ኮኑ ፡ በትልወታ ፡ አግብርት ፡ ወአ እማት ፡ እመ ፡ ሕያዋን ፡ እሙንቱ ፡ ትንሥ እሙ ፡ ወለእመ ፡ ተሠይጡ ፡ ትንሣእ ፡ ሜጠሙ ወለእመሰ ፡ ሞቱ ፡ ኢይደልዋ ፡ ላቲ ፡ ከመ ፡ ትንሣእ ፡ ሜጠሙ ፡ ወኢቤዛሆሙ ፡ እስመ ፡ መዋትያን ፡ እሙንቱ ፡ በጠባይዒሆሙ ፡ ወለ እመ ፡ ወለዱ ፡ እግብርት ፡ ወእእማት ፡ መን ፈቀ ፡ ውሉዶሙ ፡ ይኩን ፡ ላቲ ፡ ወመንፈቆሙ፡ ለወራስያን ፡ ምታ ።

፩ሺ፫፻፺፫ ወከማሁ ፡ ለእመ ፡ አምጽአት ፡ ምስሌሃ ፡ መርዓተ ፡ አግባዕ ፡ እው ፡ እልሕምተ ፡ እው ፡ እምእንስሳ ፡ ወላድያን ፡ እመ ፡ ኮኑ ፡ ሀልዋን ፡ ወኢረብኑ ፡ ይኩኑ ፡ ለብእሲት ፡ ወእመ ፡ ረብኑ ፡ ትንሣእ ፡ መንፈቀ ፡ ረባኖሙ ፡ ወእመ ሞቱ ፡ ትንሣእ ፡ ከማሁ ፡ መንፈቀ ፡ ረባኅ ፡ ወበ እምሳለ ፡ ዝ ፡ ይኩን ፡ ፍትሐ ፡ እንበብት ፡ ወዘ ይመስሎ ፡ ለዝንቱ ።

፩ሺ፫፻፺፬ ሥርዋጽ ፡ ዘነገሥት ፡ ዘ፲ ፡ መንፈቀ ፡ ረባኅ፡ ለብእሲ ፡ እስመ ፡ መዛልዕቲ ፡ ኮነት ፡ እምንዋዩ ወለእመ ፡ ሞተ ፡ ፩ዱ ፡ እምፈኀርያን ፡ ቅድመ ፡ እውስቦቱ ፡ ናሁ ፡ ተነግረ ፡ ፍትሑ ፡ በክፍል ፡ ዳግማዊ ፡ እምእንቀጸ ፡ አውስቦ ፡ በእንተ ፡ አረ ቦን ፡ ዘፈኀርያን ።

፩ሺ፫፻፺፭ ምዕራፍ ፡ ራብዕ ፡ ዘይነግር ፡ ሥርዓተ ፡ ተዋ ርሶ ፡ ወቦቱ ፡ ፪ቱ ፡ መዓርጋት ። መዓርግ ፡ ቀዳ ማዊ ፡ በእንተ ፡ ዘይወርሱ ፡ ውሉድ ፡ እምአበ ዊሆሙ ፡ ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ቀዳማዊ ፡ መዓ ርግ ፡ ዘወራስያን ። ምክንያተ ፡ ቀዲሞቶሙሰ ፡ ለውሉደ ፡ ምዉት ፡ ለወሪሶቱ ፡ እምወላድያ ኒሁ ፡ እስመ ፡ እበው ፡ እሙንቱ ፡ ምክንያተ ፡ ምጽአቶሙ ፡ ለውሉዶሙ ፡ ወምክንያተ ፡ ተረ ክቦቶሙ ፡ ወይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ምክንያተ ፡ በቍዔት ፡ ዝንቱ ፡ ከዊነ ፡ ተረክቦቶሙ ፡ ወዝ ንቱኒ ፡ ይከውን ፡ በንዋይ ።

፩ሺ፫፻፺፮ ወዓዲ ፡ እስመ ፡ ውሉድ ፡ ተወከፍያን ፡ ሕይ ወት ፡ ይሴፈውዋ ፡ ለሕይወ ፡ ወእምኔዋኒ ሆሙ ፡ ቅሩባን ፡ ለተፈልጦ ፡ እምኔሃ ፡ ወበንዋ



በመካከላቸው ፡ ከሚሆነው ፡ መጽሐፍ ፡ ዋጋዉ ፡ የታወቀ ፡ በቀለም ፡ ያገቡትም ፡ ያመ ጣቻቸው ፡ ሌሎችም ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ።

፩ሺ፫፻፺፪ በትልወቷ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ባሮች ፡ ቢሆ ኑ ፡ እነርሱም ፡ ቢኖሩ ፡ ትውሰዳቸው ። ተሸ ጠውም ፡ እንደሆነ ፡ ዋጋቸውን ፡ ትውሰድ ። ቢሞቱ ፡ ግን ፡ ዋጋቸውን ፡ ወይም ፡ ምትካቸ ውን ፡ ልትቀበል ፡ አይገባትም ። በተፈጥሮአ ቸው ፡ ሟቾች ፡ ናቸውና ። ወንዶች ፡ ባሮችና ፡ ሴቶች ፡ ባሮች ፡ ቢወልዱ ፡ የልጆቻቸው ፡ እኩ ሌቶች ፡ ለእርሷ ፡ እኩሌቶቹ ፡ ለባልዋ ፡ ወራ ሾች ፡ ይሁኑ ።

፩ሺ፫፻፺፫ እንደዚኹውም ፡ የበግ ፡ መንጋ ፡ ወይም ፡ ላሞች ፡ ወይም ፡ ከሚወልዱ ፡ እንስሶች ፡ ወገን ፡ ከእርሱዋ ፡ ጋራ ፡ ብታመጣ ፡ ያሉ ፡ ቢሆኑ ፡ ራሳቸው ፡ ባይራቡ ፡ ለሚስቲቱ ፡ ይሁኑ ። ቢራቡ የርቢያቸውን ፡ እኩሌታ ፡ ትውሰድ ፡ ቢሞቱም፡ እንዲሁ ፡ የርቢውን ፡ እኩሌታ ፡ ትውሰድ ። የን ቦችም ፡ ፍርድና ፡ ይህን ፡ የመሰለው ፡ በዚህ ፡ አምሳል ፡ ይሁን ።

፩ሺ፫፻፺፬ ሥርዋጽ ። ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ፲ ። የርቢው ፡ እኩሌታ ፡ ለባል ፡ ይገባል ። መብሏ ፡ ከገንዘቡ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ። ከተጫጨት ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ ከማግባቱ ፡ በፊት ፡ ቢሞት ፡ ስለሚተጫጩ ፡ ሰዎች ፡ ዓረቦን ፡ ከሚናገረው ፡ የጋብቻ ፡ አን ቀጽ ፡ በሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ እነሆ ፡ ፍርዱ ፡ ተነግሯል ።

፩ሺ፫፻፺፭ ፬ኛው ፡ ምዕራፍ ። ያወራረስን ፡ ሥርዓት ፡ የሚናገር ፡ ነው ። ሁለት ፡ መዓርጎች ፡ አሉት ። መጀመሪያው ፡ መዓርግ ፡ ልጆች ፡ ከአባቶቻ ቸው ፡ ስለሚወርሱ ፡ ይናገራል ። የወራሾች ፡ አንደኛ ፡ መዓርግ ፡ ይህ ፡ ነው ። የሙት ፡ ልጆች ከወላጆቹ ፡ እርሱን ፡ ለመውረስ ፡ የመቅደሚ ቸው ፡ ምክንያትስ ፡ አባቶች ፡ ለልጆቻቸው ፡ የመምጣታቸው ፡ ምክንያትና ፡ የመገኘታቸው ፡ ምክንያት ፡ ስለሆኑ ፡ ነው ። ይህ ፡ መገኛ ፡ መሆ ናቸው ፡ ጥቅም ፡ ያለበት ፡ ምክንያት ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ። ይኸውም ፡ በገንዘብ ፡ ይሆናል ።

፩ሺ፫፻፺፮ ዳግመኛ ፡ ልጆች ፡ ኑሮን ፡ የሚቀበሉ ፡ ናቸ ውና ፡ መኖርን ፡ ተስፋ ፡ ያደርጓታል ። አያቶች ፡ ግን ፡ ከእርሷ ፡ ለመለየት ፡ የተቃረቡ ፡ ናቸው ።

አንቀጽ ፡ ፵፪ ።

ዶኒ ፡ ትትወውም ፡ ሕይወት ፡ ምስለ ፡ በቀኍዒታ ። ለደቂቅኒ ፡ እንከ ፡ ይደልዎሙ ፡ ንሢአ ፡ ንዋይ ፡ እምነ ፡ እምኄዋኒሆሙ ። ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ከዊነ ፡ ተዋርሶ ፡ ይወርድ ፡ እምላዕሉ ፡ ኀበ ፡ ታሕቱ ፡ ወኢይገብዕ ፡ እምታሕቱ ፡ ኀበ ፡ ላዕሉ ዳእሙ ፡ ለእመ ፡ ተነጥአ ፡ ዘይቴሐት ፡ እም ኔሁ ፡ ወኢሀለወ ፡ ከመዝ ፡ በኀልፈተ ፡ ዘመን ።

፩ሺ፫፻፹፱ ሥርዋጽ ፡ ይትዐወቅ ፡ እስመ ፡ ፍትሐ ፡ ዐበ ይት ፡ ፍጥረታዊ ፡ እስመ ፡ ዐበይት ፡ ይመውቱ ፡ እምቅድመ ፡ ንኡሳን ፡ በሕይወቶሙ ። ወካ ዕበ ፡ ዝክረ ፡ አበው ፡ ይትረኃ ፡ በውሉዶሙ ፡ ለአበዊሆሙ ፡ ወእሙንቱ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይረ ስዎሙ ፡ ወምክንያቱ ፡ ተዋርሶቱ ፡ ሰወለት ፡ ከመ ፡ ወልድ ፡ ኮነ ፡ በሐዲስ ፡ ሕግ ፡ ወአኮ ፡ በብሉይ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ እስመ ፡ ብእሲ ፡ ወብእሲት ፡ ፩ዱ ፡ እሙንቱ ፡ በክርስቶስ ፡ ወዓዲ ፡ በተዋርሶ ፡ ይከውኑ ፡ ዕሩ ያነ ። ወይእቲ ፡ ከዊነ ፡ ወልድና ፡ ወይደልዎሙ ለውሉድ ፡ ወኵሉ ፡ ለለ፩ዱ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ መክፈልቱ ፡ ላዕለ ፡ ዘይደልዎ ፡ ለኵልኡ ፡ ወም ክንያቱ ፡ ቀዲሞቶሙስ ፡ ለውሉድ ፡ እምውሉ ዶሙ ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ይቀርቡ ፡ እምኔ ሆሙ ።

፩ሺ፫፻፺ መክ ፡ ፩ዱ ፡ ቍወ፫ቱ ፡ ወዘሂ ፡ ሞተ ፡ ዘእን በለ ፡ ይጽሐፍ ፡ ትእዛዞቲሁ ፡ ውሉዱ ፡ ውሉደ ፡ ተባዕት ፡ ወአንስት ፡ ለይረሱ ፡ በዕሩና ። መጽ ፡ እመኒ ፡ ኮኑ ፡ ፍጹማነ ፡ በአብ ፡ ወእም ፡ አው ፡ ዘኢ.ፍጹማን ። ጠስ ፡ ፴ ፡ ወለእመኒ ፡ ኮነ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ጸሙመ ፡ አው ፡ በሃመ ፡ እመኒ ፡ ኮኑ ፡ ቅሩባነ ፡ አው ፡ ኢ.ቅሩባነ ።

፩ሺ፫፻፺፩ ጠስ ፡ ፴ ፡ መክ ፡ ቍወ፫ቱ ፡ ወለእመ ፡ ተወ ሰበት ፡ ወለት ፡ እምድኅረ ፡ ነሥአት ፡ ትል ወታ ፡ እምወላዲዮሃ ፡ ይትኀለቍ ፡ ትልወታ ፡ ውስተ ፡ ርስታ ፡ እመኒ ፡ ሠርዐ ፡ አቡሃ ፡ በሕ ይወቱ ፡ ወእመኒ ፡ ኢሠርዐ ፡ ወተስናአዎ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅሒም ፡ በዝንቱ ፡ ከመ ፡ ለእመ ፡ ፈደፈደ ፡ ውእቱ ፡ እምዘይደልዋ ፡ እም ተዋርሶ ፡ ኢትኅሥሥ ፡ ውሳኬ ፡ ወእመኒ ፡ ሐጸ፡ ትንሣእ ፡ ፍጻሜ ።

፩ሺ፫፻፺፪ መጽ ፡ ፲፪ ወ፪ቱ ፡ ወዘሂ ፡ ተወልደ ፡ እምእግዓ ዚኡ ፡ እምድኅረ ፡ ጸሐፈ ፡ ትእዛዝ ፡ ይረስ ፡ ምስለ ፡ አኃዊሁ ፡ ወይኩን ፡ ከመ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔ ሆሙ ።

ስለ ፡ ርስት ።

በገንዘብም ፡ ከጥቅሟ ፡ ጋር ፡ ኑሮ ፡ ትጸናለች ። እንግዲህ ፡ ለልጆችም ፡ ካያቶቻቸው ፡ ገንዘብ ፡ መውሰድ ፡ ይገባቸዋል ። ስለዚህ ፡ ያወራረስ ፡ ሁኔታ ፡ ከላይ ፡ ወደታች ፡ ይወርዳል ። ከታች ፡ ወደላይ ፡ አይመለስም ። ከእነርሱ ፡ ወደታች ፡ የሚሆን ፡ ቢታጣ ፡ ነው ፡ እንጂ ። በዘመን ፡ መተላለፍ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ የለም ።

፩ሺ፫፻፹፱ ሥርዋጽ ። የታላላቆች ፡ ፍርድ ፡ በተፈጥሮ ፡ ነውና ፡ ታናናሾች ፡ በሕይወታቸው ፡ ሳሉ ፡ ታላላቆች ፡ ስለሚሞቱ ፡ ይታወቃል ። ዳግመ ኛም ፡ ያባቶች ፡ ስም ፡ በእባቶች ፡ ልጆች ፡ ይቀ ራል ። (ይጠራል) ፡ እነርሱም ፡ ይወርሷቸው ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ። ሴት ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ የመውረሷ ፡ ምክንያት ፡ በሐዲስ ፡ ሕግ ፡ ተጀመረ በብሉይ ፡ ግን ፡ አይደለም ። ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ ሴ ትና ፡ ወንድ ፡ በክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ እንዳለ (ገላ ፡ ፫ ፡ ፳፰) ። ዳግመኛም ፡ ባወራረስ ፡ ትክ ክል ፡ ይሆናሉ ። ይህችውም ፡ የልጅነት ፡ ሁኔታ ናት ። ለልጆች ፡ ሁሉ ፡ ለእያንዳንዳንዱ ፡ ድር ሻው ፡ ለወንድሙ ፡ በሚገባው ፡ ሊሆን ፡ ይገባ ቸዋል ። ልጆች ፡ ከልጆቻቸው ፡ የመቅደማቸው ምክንያት ፡ እነርሱ ፡ ከእነርሱ ፡ የሚቀርቡ ስለሆነ ፡ ነው ።

፩ሺ፫፻፺ መክ ፡ ፩ ፡ ቍ፫ ። ትእዛዙን ፡ ሳይጽፍ ፡ የሞተ ፡ ሰውም ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆችን ፡ ቢተው ፡ በ ትክክል ፡ ይውረሱ ። መጽ ፡ ፯ ። በእባትና ፡ በእ ናት ፡ ፍጹማን ፡ (አንድ) ፡ ቢሆኑ ፡ ወይም ፡ ፍጹ ማን ፡ ባይሆኑ ። ጠስ ፡ ፴ ። ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ ደንቆሮ ፡ ወይም ፡ ዲዳ ፡ ቢሆን ፡ ቅርቦችም ፡ ቢሆኑ ፡ ወይም ፡ ሩቆች ፡ ቢሆኑ ።

፩ሺ፫፻፺፩ ጠስ ፡ ፴ ። መክ ፡ ቍ፫ ። ሴት ፡ ልጅ ፡ ከወላ ጆቿ ፡ ትልወቷን ፡ ከተቀበለች ፡ በኋላ ፡ ብታ ገባ ፡ ትልወቷ ፡ ከርስቷ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ይቈ ጠራል ። እባቷ ፡ በሕይወት ፡ ሳለ ፡ ቢያዝዝም ፡ ባያዝዝም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መስማማት ፡ በዚህ ፡ ይጸናል ። ይህስ ፡ መውረስ ፡ ከሚገባት ፡ ገንዘብ ፡ ቢበዛ ፡ ጭማሪ ፡ አትፈልግ ። ቢያን ስም ፡ ጨርሳ ፡ ትውሰድ ።

፩ሺ፫፻፺፪ መጽ ፡ ፲፪ ። ትእዛዝ ፡ ከተጻፈ ፡ በኋላ ፡ ነፃ ፡ ከወጣችው ፡ አገልጋይ ፡ የተወለደ ፡ ልጅም ፡ ከወንድሞቹ ፡ ጋራ ፡ ይውረስ ፡ ከእነርሱም ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ይሁን ።

እንቀጽ ፡ ፵፪ ።

፩ሺ፫፻፶፱ መክ ፡ ፶ወ፬ቱ ፡ ወእለሰ ፡ ተወልዱ ፡ እምተዋ ስቦ ፡ ዘእበሳ ፡ ዘከመ ፡ ብእሲተ ፡ እኁ ፡ ወእ ኀተ ፡ ብእሲት ፡ ወከመ ፡ እኅተ ፡ እብ ፡ ወእኅተ፡ እም ፡ ወብእሲተ ፡ እብ ፡ ወዕቅብቱ ፡ ኢይረ ስዎሙ ፡ ለአበዊሆሙ ፡ ዘእንበለ ፡ በጽሒፈ ፡ ትእዛዝ ፡ ወባሕቱ ፡ ዘይወርስዎሙ ፡ እለ ፡ ተወ ልዱ ፡ ሎሙ ፡ እምብእሲት ፡ ሕጋዊት ፡ ብዉሕ፡ መክ ፡ ፶ወ፰ቱ ፡ ወለእመ ፡ እዘዘ ፡ ሎሙ ፡ እቡ ሆሙ ፡ በምንትኒ ፡ ወእፍቀረ ፡ ከመ ፡ ያውር ሶሙ ፡ ምስለ ፡ እኃዊሆሙ ፡ በዕሪና ፡ ይደሉ ፡ ሎቱ ፡ ዝንቱ ።

፩ሺ፫፻፷ መዓርግ ፡ ዳግማዊ ፡ በእንተ ፡ ዘይወርስዎ ፡ ተባዕት ፡ ወእንስት ፡ እምውሉደ ፡ ውሉድ ፡ ተባዕት ፡ ባሕቲቶሙ ፡ እምነ ፡ እምኀዋኒሆሙ። ጠስ ፡ ዘ፴ ፡ መጅ ፡ ዘ፲ወ፪ቱ ፡ ወውሉደ ፡ ውሉድ ፡ ይረሱ ፡ እምኀዋኒሆሙ ፡ ወእመኒ ፡ ኮኑ ፡ ተባዕተ ፡ እው ፡ እንስተ ፡ ወይከልኡ ፡ እበው ፡ እምኀዋኒሆሙ ።

፩ሺ፫፻፷፩ ሥርዋጽ ፡ ጠስ ፡ ዘ፴ ፡ ወለእመ ፡ ሞተ ፡ እም ኄው ፡ ወሎቱ ፡ ወልድ ፡ ወዓዲ ፡ ውሉድ ፡ እም ካልእ ፡ ወልዱ ፡ ውሉደ ፡ ወልዱ ፡ ይባኡ ፡ ውስተ ፡ መክፈልተ ፡ እቡሆሙ ፡ ወይረሱ ፡ ዕሩየ ፡ ምስለ ፡ እኀወ ፡ እቡሆሙ ፡ ወይንሥኡ ፡ ዘኮነ ፡ ይነሥእ ፡ እቡሆሙ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ሕያወ ። ወለእመኒ ፡ ኮኑ ፡ ተባዕተ ፡ እው ፡ እን ስተ ፡ ለእመኒ ፡ ታሕተ ፡ ምግብና ፡ እው ፡ ውፁ እነ ፡ እምግብና ። ወዝንቱ ፡ ፍትሕ ፡ ዘኢይት ገበር ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንነ ፡ እስመ ፡ ዘተ ነግረ ፡ በሥርው ፡ ይኄይስ ፡ እምዘ ፡ ሀለወ ፡ ውስተ ፡ ዛቲ ፡ ሥርዋጽ ፡ እስመ ፡ ውሉዱ ፡ ይቀ ርቡ ፡ እምውሉደ ፡ ውሉዱ ፡ ወርስት ፡ ለዘይቀ ርብኬ ፡ ይደሉ ።

፩ሺ፫፻፷፪ ምዕራፍ ፡ ኃምስ ። በእንተ ፡ ዘይወርስ ፡ እብ ፡ እምውሉዱ ፡ ወይእቲ ፡ መዓርግ ፡ ኃልሲት ፡ በእ ንተ ፡ ዘይቀድም ፡ እብ ፡ እምእኃዊሁ ፡ ወቅድ መቲሰ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ዘይቀርብ ። እስመ ፡ ማእከለ ፡ እብ ፡ ወወልዱ ፡ መዓርግ ፡ እሐቲ ፡ ወማእከለ ፡ እኁሁ ፡ ወእኍሁ ፡ ፪ቲ ፡ መዓርግ ፡ ዘውእቱ ፡ ፪ቱ ፡ ልደት ። ወዳግምኒ ፡ እስመ ፡ እብ ፡ ውእቱ ፡ ምክንያተ ፡ ተረክቦተ ፡ ውሉዱ ፡ ወርክበተ ፡ ንዋይ ፡ ወተቀዋሚ ፡ ላዕለ ፡ ርክበተ ፡ ሰብእ ፡ ንዋይ ፡ ወእኍሁሰ ፡ ኢኮነ ፡ ውእቱ ፡ ምክ ንያተ ፡ ተረክቦተ ፡ እኁሁ ፡ እስመ ፡ እብ ፡ ዘው

ስስ ፡ ርስት ።

፩ሺ፫፻፶፱ መክ ፡ ፶፰ ። ከበደል ፡ (ከሕግ ፡ ውጭ) ፡ ጋብቻ የተወለዱ ፡ ግን ፡ ከወንድም ፡ ሚስት ፡ ከሚ ስት ፡ እኅት ፡ ከአባት ፡ እኅት ፡ ከእናትም ፡ እኅ ት ፡ ከአባት ፡ ሚስት ፡ ከዕቁባቱም ፡ የተወለዱ ፡ በማዘዣ ፡ ደብዳቤ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አባቶቻ ቸውን ፡ አይውረሱዋቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ የሚ ወርሷቸውስ ፡ ከሕግ ፡ ሚስት ፡ የተወለዱ ፡ ቢሆኑ ፡ አግባብ ፡ ነው ። መክ ፡ ፶፰ ። አባታ ቸው ፡ በማናቸውም ፡ ቢያዝዝላቸው ፡ ከወንድ ሞቻቸው ፡ ጋር ፡ በትክክል ፡ ሊያወርሳቸው ፡ ቢወድ ፡ ይህ ፡ ለእርሱ ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ፫፻፷ ሁለተኛ ፡ መዓርግ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ከወን ዶች ፡ የልጅ ፡ ልጆች ፡ ብቻቸውን ፡ ካያቶቻቸው ስለሚወርሱት ፡ ይናገራል ፡ ጠስ ፡ ፴ ። መጅ ፡ ፲፪ ። የልጅ ፡ ልጆች ፡ አያቶቻቸውን ፡ ይውረሱ። ወንዶችና ፡ ሴቶችም ፡ ቢሆኑ ። አያቶቻቸው ፡ አባቶችን ፡ ይከለክሉ ።

፩ሺ፫፻፷፩ ሥርዋጽ ፡ ጠስ ፡ ፴ ። አያት ፡ ቢሞት ፡ ልጅም ቢኖረው ፡ ዳግመኛም ፡ ከሌላ ፡ ልጁ ፡ የተወ ለዱ ፡ የልጅ ፡ ልጆች ፡ ቢኖሩ ፡ በአባታቸው ፡ ድርሻ ፡ ገብተው ፡ ከአባታቸው ፡ ወንድም ፡ ጋራ ፡ በትክክል ፡ ይውረሱ ። አባታቸው ፡ ደኅና ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ይወስደው ፡ የነበረውን ፡ ይውሰዱ ፡ ወንዶች ፡ ወይም ፡ ሴቶች ፡ ቢሆኑ ፡ በመተዳደር ፡ ስር ፡ ቢሆኑም ፡ ወይም ፡ ከመ ተዳደር ፡ የወጡ ፡ ቢሆኑ ። ይህ ፡ ፍርድ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የማይሠራ ፡ ነው ። በዚች ፡ ሥርዋጽ ፡ ካለው ፡ በሥር ፡ (በመጀመሪያ) ፡ የተ ነገረው ፡ ይበልጣልና ። ከልጅ ፡ ልጆቹ ፡ ልጆቹ፡ ይቀርባሉና ። ርስትም ፡ ለሚቀርብ ፡ ይገባል ።

፩ሺ፫፻፷፪ አምስተኛ ፡ ምዕራፍ ። አባት ፡ ከልጆቹ ፡ ስለ ሚወርሰው ፡ ይናገራል ። ይህችውም ፡ ፫ኛ ፡ መዓርግ ፡ ናት ። አባት ፡ ከወንድሞቹ ፡ ስለሚ ቀድም ፡ ነው ። መቅደሙም ፡ እርሱ ፡ የሚቀ ርብ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ። በአባትና ፡ በልጁ ፡ መካ ከል ፡ መዓርግ ፡ አንዲት ፡ ናትና ። በወንድሙና፡ በወንድሙ ፡ መካከል ፡ ግን ፡ ፪ ፡ መዓርግ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ፪ትውልድ ፡ ነው ። ዳግመ ኛም ፡ አባት ፡ ለልጆቹ ፡ መገኘትና ፡ ለገንዘቡ ፡ መገኘት ፡ ምክንያት ፡ እርሱ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ። የገንዘብ ፡ ሰዎችም ፡ በመገኘታቸው ፡ ይጸናል ።

አንቀጽ ፡ ፶፪ ።

እት ፡ ሥርወ ፡ ለንዋይ ፡ ይደልዎ ፡ ነጊአት ፡ ።

፩ሺ፫፻፶፯ ወካዕበ ፡ ዘይበዝኅ ፡ ይኩን ፡ ለአብ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ዘወሀበ ፡ ውእተ ፡ ንዋየ ፡ ለወልዱ ፡ ወተመይጦቱ ፡ ኀቤሁኬ ፡ ይደሉ ፡ ወበዝንቱ ፡ ካዕበ ፡ ይደሉ ፡ አቅድሞ ፡ አብ ፡ እምእም ። ወዓዲ ፡ ካዕበ ፡ እስመ ፡ ብእሲት ፡ ተፈጥረት ፡ በእንተ ፡ ብእሲ ፡ ወዘሂ ፡ ተፈጥረ ፡ በእንተ ፡ ካልእ ፡ ውእቱኬ ፡ ይቴሐት ፡ በክብር ፡ እምዝኩ ፡ ካልእ ፡ ወካዕበ ፡ እስመ ፡ እም ፡ ከመ ፡ ሙዳይ ፡ ወከመ ፡ ምድር ፡ ለዘርእ ። ወፈድፋደሰ ፡ ይገብእ ፡ ንዋይ ፡ ካዕበ ፡ ኀበ ፡ እኍ ፡ ወራሲ ፡ እምኀበ ፡ አብ ፡ ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ምክንያቱ ፡ አቅድሞ ፡ አብ ፡ እምአኀው ፡ ወእም ።

፩ሺ፫፻፶፰ መክ ፡ ፩ዱ ፡ መጅ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ለእመ ፡ ሞተ ፡ ፩ዱ ፡ ወእልቦቱ ፡ ሎቱ ፡ ውሉድ ፡ ወኢ ፡ ውሉደ ፡ ውሉድ ፡ ወኢጸሐፈ ፡ ትእዛዛቲሁ ፡ ወቦኑ ፡ ሎቱ ፡ አብ ፡ ወእም ፡ ይከውን ፡ ርስቱ ፡ ለአበዊሁ ፡ ባሕቲቶሙ ።

፩ሺ፫፻፶፱ ምዕራፍ ፡ ሳድስ ። ቦቱ ፡ ፬ቱ ፡ መዓርጋት ፡ በእንተ ፡ ዘይወርስዎ ፡ ፍጹማነ ፡ ልደት ፡ እምአኀው ፡ ወአኃት ፡ ወበይናቲሆሙ ፡ ወዘሂ ፡ ይወርስዎ ፡ እለ ፡ ኢኮኑ ፡ ፍጹማነ ፡ ልደት ። ወሥርዓቶሙ ፡ ለእምኄዋን ፡ ምስለ ፡ አኀው ፡ ወአኃት ፡ ወርስተ ፡ እም ፡ ወሥርዓታ ፡ ወተዋርሶ ፡ ውሉደ ፡ አኀው ። ረሰይዎሙ ፡ ለአኀው ፡ እምድኅረ ፡ አብ ፡ እስመ ፡ ውእቶሙ ፡ ውሉዱ ፡ ወውሉዱኬ ፡ ይቀርቡ ፡ ኀቤሁ ፡ እምካልእኒሆሙ ፡ ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ምክንያቱ ፡ አቅድሞቱ ፡ አኀው ፡ እምነ ፡ እምኄዋን ። እስመ ፡ ምዉት ፡ ወአኀዊሁ ፡ ዕሩያን ፡ እሙንቱ ፡ በልደት ፡ ዘይቀርብ ፡ ኀበ ፡ አብ ፡ ወውእቱ ፡ ክዋኔ ፡ ትዝምድና ፡ ዘውሉድ ፡ ወዝምድተ ፡ እምኄዋን ፡ ኀበ ፡ ወልደ ፡ ምዉት ፡ ዝምድተ ፡ አብና ፡ ወወልድና ፡ በተዋርሶት ፡ ነዋ ፡ ያቀድም ፡ በትእዛዝ ፡ እም አብ ። ወካዕበ ፡ እስመ ፡ እምኄዋን ፡ ቅሩባን ፡ ለሐዊር ፡ እምዛቲ ፡ ሕይወት ፡ ወውሉደ ፡ ውሉዶሙኒ ፡ እለ ፡ እሙንቱ ፡ አኀው ፡ ተቀባልያን ፡ ውእቶሙኬ ፡ እለ ፡ ይፈትይዎ ፡ ፈድፋዴ ፡ ለንዋይ ።

፩ሺ፫፻፷ መዓርግ ፡ ራብዕት ፡ መክ ፡ ዘ፲ወ፬ቱ ፡ እመቦ ፡

ስለ ፡ ርስት ።

ወንድም ፡ ግን ፡ ለወንድሙ ፡ መገኘት ፡ ምክንያት ፡ አልሆነም ። አባት ፡ ለገንዘቡ ፡ ሥሩ ፡ (መገኛው) ፡ ስለሆነ ፡ ሊወስደው ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ፫፻፶፯ ዳግመኛም ፡ የሚበዛው ፡ ለአባት ፡ ይሁን ። ይህን ፡ ገንዘብ ፡ ለልጁ ፡ የሰጠ ፡ እርሱ ፡ ነውና ። ወደእርሱም ፡ መመለሱ ፡ ይገባል ። ዳግመኛም ፡ በዚህ ፡ ከእናት ፡ አባትን ፡ ማስቀደም ፡ ይገባል ። ዳግመኛም ፡ ሴት ፡ ስለወንድ ፡ ተፈጥራለችና ። ስለ ፡ ሌላ ፡ የተፈጠረ ፡ ከዚያ ፡ ከሌላው ፡ በክብር ፡ ዝቅ ፡ ይላል ። ዳግመኛም ፡ እናት ፡ እንደ ፡ ሣጥንና ፡ ለዘርእ ፡ እንደ ፡ ተዘጋጀ ፡ ምድር ፡ (እርሻ) ፡ ናትና ። ይልቁንም ፡ ገንዘብ ፡ ካባት ፡ ወደሚወርስ ፡ ወንድም ፡ እነሆ ፡ ይመለሳል ። አባትን ፡ ከወንድሞችና ፡ ከእናት ፡ የማስቀደም ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፡ ነው ።

፩ሺ፫፻፶፰ መክ ፡ ፩ ። መጅ ፡ ፲፪ ። አንድ ፡ ሰው ፡ ቢሞት ለእርሱም ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ባይኖሩት ፡ ትእዛዙንም ፡ ባይጽፍ ፡ አባትና ፡ እናትም ፡ ቢኖሩለት ፡ ርስቱ ፡ ለአባቱ ፡ ብቻ ፡ ይሆናል ።

፩ሺ፫፻፶፱ ስድስተኛ ፡ ምዕራፍ ። አራት ፡ መዓርጋት ፡ አሉበት ። ከወንድሞችና ፡ ከእኅቶች ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ በልደት ፡ ፍጹማን ፡ (አንድ) ፡ የሆኑትና ፡ በልደት ፡ ፍጹማን ፡ (አንድ) ፡ ያልሆኑት ስለሚወርሱት ፡ ከወንድሞችና ፡ ከእኅቶች ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ አያቶች ፡ ሥርዓት ፡ ስለእናትም ፡ ርስትና ፡ ስለሥርዓቷ ፡ ስለወንድሞችም ፡ ልጆች ፡ መውረስ ፡ ይናገራል ። ወንድሞችን ፡ ከአባት ፡ ቀጥለው ፡ አደረጓቸው ። እነርሱ ፡ ልጆቹ ፡ ናቸውና ፡ ከሌሎቹም ፡ ለእርሱ ፡ ልጆቹ ይቀርቡታልና ። ከአያቶች ፡ ወንድሞችን ፡ የማስቀደም ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፡ ነው ። ሟቹና ፡ ወንድሞቹ ፡ ወደ ፡ አባት ፡ በሚቀርብ ፡ ልደት ፡ ትክክል ፡ ናቸውና ። ይኸውም ፡ የልጆች ፡ ዝምድናና ፡ በሟች ፡ ልጅ ፡ ዘንድ ፡ ያያቶች ፡ ዝምድና ፡ የአባትነትና ፡ የልጅነት ፡ ዝምድና ፡ ነው ። ባወራረስ ፡ ጊዜ ፡ እነሆ ፡ በትእዛዝ ፡ ከአባት ፡ ያስቀድማል ። ዳግመኛ ፡ አያቶች ፡ ከዚች ፡ ሕይወት ፡ ለመሄድ ፡ የተቃረቡ ፡ ናቸውና ። የልጆቻቸው ፡ ልጆችም ፡ ተቀባዮች ፡ ወንድሞች ፡ ናቸው ። ገንዘብን ፡ አጅግ ፡ የሚሹት ፡ እነርሱ ፡ ናቸው ።

፩ሺ፫፻፷ ፬ኛ ፡ መዓርግ ። መክ ፡ ፲፬ ። ልጅ ፡ ወይም ፡

አንቀጽ ፡ ፵፪ ።

ዘእልቦቱ ፡ ወልድ ፡ ወኢአብ ፡ ለይረስዎ ፡ አኃዊሁ ፡ ወእኅቲሁ ፡ ወእሙ ፡ ባሕቲቱ ፡ ለእም ፡ ከመ ፡ መክፈልተ ፡ ፩ዱ ፡ እምውሉዳ ፡ በሰሪና ።

፩ሺ፫፻፶፩ ጠስ ፡ ዘ፴ ፡ አኃው ፡ ወአኃት፡ ፍጹማነ ፡ ልደት ፡ ዘውእቶሙ ፡ እለ ፡ ተወልዱ ፡ እም፩ዱ፡ አብ ፡ ወእምእሐቲ ፡ እም ፡ ይረሱ ፡ በዕሪና ፡ በበ ይናቲሆሙ ።

፩ሺ፫፻፶፪ መዓርግ ፡ ኃምሲት ፡ መዓርግ ፡ ሳድሲት ፡ ጠስ ፡ ዘ፴ ፡ ወለእመ ፡ አልቦቱ ፡ አኃው ፡ ፍጹማን ፡ ዘእምእቡሁ ፡ ወእሙ ፡ ይረስዎ ፡ አኃዊሁ ፡ እለ ፡ ፍሉጣን ፡ በልደቶ ፡ አብ ፡ ወእመኒ፡ በእም ። ወምክንያተ ፡ ዝንቱ ፡ እስመ ፡ እለ ፡ ይዘመዱ ፡ ምስሌሁ ፡ ይቀርቡ ፡ እምእለ ፡ ኢኮኑ እምወላድያኒሁ ፡ ይደሉ ፡ እምዝምደት ፡ ካልእት ፡ ዘኢትትፌጸም ።

፩ሺ፫፻፶፫ መጅ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ወእኅውኒ ፡ ዘእምአብ ፡ ይቅድም ፡ እምነ ፡ እኅው ፡ ዘእምእም ፡ ወምክንያቱስ ፡ እስመ ፡ ዘይትወለድ ፡ እምአብ ፡ ሎቱ ፡ ተዘምዶ ፡ እመንገለ ፡ ፆታ ፡ ቀዳሚት ። ወለእመ ፡ አልቦቱ ፡ ለመዋቲ ፡ ወላድያን ፡ ይረስዎ ፡ እምኔሁ ፡ ወእምኔሆሙ ፡ ምስለ ፡ አኃዊሁ ፡ ወእኃቲሁ ፡ ፫ቲሆሙ ።

፩ሺ፫፻፶፬ ወበዝንቱ ፡ ቀኖና ፡ ኢተፈልጠ ፡ ቦቱ ፡ ግብሮሙ ፡ ለእሉ ፡ እምኔዋን ፡ እለ ፡ እሙንቱ ፡ እምኔዋን ፡ ዘአብ ፡ ወእምኔዋን ፡ ዘእም ፡ ወቀኖናስ ፡ ተዋርሶ ፡ ለእምኔው ፡ ዘእምአብ ፡ እምቅድመ ፡ እምኔው ፡ ዘእምእም ። ወይደሉ ፡ ካዕበ ፡ በዝንቱ ፡ አንቀጽ ፡ ከመ ፡ ይቅድሙ ፡ እምኔዋን ፡ ዘአብ ፡ እምነ ፡ እምኔዋን ፡ ዘእም ፡ ወዝንቱስ ፡ ሶበ ፡ ኮኑ ፡ አኃው ፡ እም፩ዱ ፡ አብ ፡ ወእምእሐቲ ፡ እም ። ወእመኒ ፡ ኮኑ ፡ አኃው ፡ ዘእምአብ ፡ ባሕቲቱ ፡ ይረስዎ ፡ እምኔዋኒሁ ፡ ዘእቡሁ ፡ ባሕቲቶሙ ፡ ወለእመ ፡ ኮኑ ፡ አኃው ፡ ዘእም ፡ ባሕቲታ ፡ ይረሱ ፡ እምኔዋን ፡ ዘእም እም ፡ ባሕቲታ ።

፩ሺ፫፻፶፭ ወለእመሰኬ ፡ ረሰይዋ ፡ ለእመ ፡ ምዉት ፡ ከመ ፡ ፩ዱ ፡ እምአኃዊሁ ፡ ወአኃቲሁ ፡ ኢይክልእ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ እመ ፡ ኮኑ ፡ ዘእምአብ ወእም ፡ አው ፡ እመ ፡ ኢኮኑ ፡ አላ ፡ ትረስ ፡

ስለ ፡ ርስት ።

አባት ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ወንድሞቹና ፡ እኅቶቹ ፡ እናቱም ፡ ይውረሱት ። ነገር ፡ ግን ፡ ለእናት ፡ ከልጆቿ ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ድርሻ ፡ በትክክል ፡ ይገባታል ።

፩ሺ፫፻፶፩ ጠስ ፡ ፴ ። በልደት ፡ ፍጹማን ፡ (አንድ) ፡ የሆኑ ፡ እኒኸውም ፡ ከአንድ ፡ አባትና ፡ ከአንዲት ፡ እናት ፡ የተወለዱ ፡ እርስበርሳቸው ፡ በትክክል ፡ ይውረሱ ።

፩ሺ፫፻፶፪ አምስተኛዪቱ ፡ መዓርግና ፡ ስድስተኛዪቱ ፡ መዓርግ ። ጠስ ፡ ፴ ። ከ፩ ፡ አባትና ፡ ከ፩ዲት ፡ እናት ፡ የተወለዱ ፡ ፍጹማን ፡ ወንድሞች ፡ ባይኖሩት ፡ ከአባት ፡ ወይም ፡ ከእናት ፡ በመወለድ ፡ የተለዩ ፡ ወንድሞቹ ፡ ይውረሱት ። የዚህም ፡ ምክንያቱ ፡ ከወላጆቹ ፡ ካልሆኑት ፡ (ካልተወለዱት) ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ የሚዛመዱ ፡ (የሚወለዱ) ፡ ፍጹም ፡ ካልሆነች ፡ ከሌላዪቱ ፡ ዝምድና ፡ ለእባት ፡ ልጅ ፡ ይገባል ።

፩ሺ፫፻፶፫ መጅ ፡ ፲፪ ። ከእናት ፡ ከሚወለድ ፡ ወንድም፡ ይልቅ ፡ ከአባት ፡ የሚወለድ ፡ ወንድም ፡ ይቅደም ። ምክንያቱም ፡ ከአባት ፡ የሚወለድ ፡ ከፊተኛዪቱ ፡ ወገን ፡ ተዘምዶ ፡ አለውና ። ለሟች ፡ ወላጆች ፡ ባይኖሩት ፡ ወንድ ፡ እያቱና ፡ ሴት ፡ እያቱ ፡ ከወንድሞቹና ፡ ከእኅቶቹ ፡ ጋራ ፡ ፫ቱም ይውረሱት ።

፩ሺ፫፻፶፬ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ የእሊህ ፡ ያያቶች ፡ ሥራ ፡ አልተለየም ። እኒኸውም ፡ በአባት ፡ በኩል ፡ ያሉ ፡ እያቶችና ፡ በእናት ፡ በኩል ፡ ያሉ ፡ እያቶች ፡ ናቸው ። በትእዛዝ ፡ ግን ፡ በእናት ፡ በኩል ካለ ፡ እያት ፡ አስቀድሞ ፡ በአባት ፡ በኩል ፡ ላለ ፡ እያት ፡ መውረስ ፡ ይገባል ። ዳግመኛም ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ በእናት ፡ በኩል ፡ ካሉ ፡ እያቶች ፡ በአባት ፡ በኩል ፡ ያሉ ፡ እያቶች ፡ ሊቀድሙ ፡ ይገባል ። ይኸውም ፡ ከአንድ ፡ አባትና፡ ከአንዲት ፡ እናት ፡ የተወለዱ ፡ ወንድማማቾች ፡ ቢሆኑ ፡ ነው ። ከአባት ፡ ብቻ ፡ የተወለዱ ፡ ወንድማማቾች ፡ ቢሆኑ ፡ በአባቱ ፡ ብቻ ፡ በኩል ፡ ያሉ ፡ እያቶች ፡ ይውረሱት ። ከእናት ፡ ብቻም ፡ የተወለዱ ፡ ወንድማማቾች ፡ ቢሆኑ ፡ በእናት ፡ ብቻ ፡ በኩል ፡ ያሉ ፡ እያቶች ፡ ይውረሱ ።

፩ሺ፫፻፶፭ የሟቹን ፡ እናት ፡ ከወንድሞቹና ፡ ከእኅቶቹ ፡ እያንዳንዱ ፡ ቢያደርጓት ፡ ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ አይከለከላት ። ከአባትና ፡ ከእናት ፡ የተወለዱ ፡ ቢሆኑ ፡ ወይም ፡ ባይሆኑ ፡ ከእነርሱ ፡ እንደ ፡

አንቀጽ ፡ ፵፪ ።

ምስለ ፡ ዘሰሙ ፡ ከመ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ።
ወሶበ ፡ ኢተረክበ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ወራሲ ፡
ትረስ ፡ እኅት ፡ በመክፈ ፡ እኁሃ ፡ ወያትከልኡ ፡
ደቂቀ ፡ አኃው ፡ እስመ ፡ ቀኖና ፡ ትኤዝዝ ፡ ላቲ ፡
ከመ ፡ ትትዐረይ ፡ ምስለ ፡ ፩ዱ ፡ እምነ ፡ እሉ ፡
አኃው ፡ ወእኁኒ ፡ ይከላእ ፡ ውሉዶ ፡ እስመ ፡
ይእቲ ፡ ትቀርብ ፡ ኀበ ፡ እምኔው ።

፩ሺ፫፻፷፯ መከ ፡ ፹ወ፰ቱ ፡ ወእም ፡ ምስለ ፡ አኃወ ፡
አብ ፡ ወውሉደ ፡ እኃወ ፡ አብ ፡ ፫ቲሆሙ ፡ ይት
ካፈሉ ።

፩ሺ፫፻፷፰ መዓርግ ፡ ሳብዒት ፡ ወፍትሑስ ፡ ለዘይቀርብ
ኀበ ፡ አብ ፡ ይቀርብ ፡ ወበአማሬ ፡ ተዋርሶ ፡
ወልደ ፡ ወልዱ ፡ እምድኅረ ፡ ወልዱ ፡ ወወረሰ ፡
ወልደ ፡ አኀወ ፡ እብ ፡ እምድኅረ ፡ አኀወ ፡
አብ ፡ ይረስ ፡ በዕሪና ፡ ተባዕት ፡ ወአንስት ፡
እለ ፡ እምውሉደ ፡ አኃው ፡ እሙንቱ ፡ እምድኅረ
አኃው ፡ ወአኃት ፡ በከመ ፡ ተሠርዐ ፡ በአንተ ፡
አኃው ። ተዐውቀ ፡ ቅድመተ ፡ ውሉደ ፡ ፍጹ
ማን ፡ እለ ፡ ተወልዱ ፡ እም፩ዱ ፡ አብ ፡ ወእም
እሐቲ ፡ እም ፡ እምዘ ፡ ኢፍጹማን ፡ ወእቅድሞተ
ውሉድ ፡ ዘእም ፡ አብ ፡ ባሕቲቱ ፡ እምነ ፡
ውሉድ ፡ ዘእም ፡ እም ፡ ባሕቲታ ፡ ወይነብር ፡
ዘይመርሕ ፡ በአንተ ፡ ውሉደ ፡ አኃው ፡ እምድ
ኅሬሆሙ ።

፩ሺ፫፻፷፱ሥርዋጽ ፡ ጠስ ፡ ፴ ፡ ወለእመ ፡ ቦቱ ፡ ለዘ
ሞተ ፡ እኁ ፡ ዘእምአቡሁ ፡ ወእሙ ፡ ዘኖሁ ፡
አዕረፈ ፡ ቅድሜሁ ፡ ወቦቱ ፡ ውሉድ ፡ ይረሱ ፡
እሙንቱ ፡ ምስለ ፡ አኃወ ፡ አቡሆሙ ፡ ዘውእ
ቶሙ ፡ አኃዊሁ ፡ ለዘሞተ ፡ እለ ፡ ተወልዱ ፡
እምአቡሁ ፡ ወእሙ ፡ ወይባእ ፡ ውስተ ፡ ዕፃሁ ፡
ለአቡሆሙ ፡ ወይንሥኡ ፡ ዘከነ ፡ አቡሆሙ ፡
ሀለዎ ፡ ይንሣእ ፡ በሕይወቱ ፡ ወየቅድምዎሙ ፡
እምኢኃው ፡ ዘኢኮኑ ፡ እምአብ ፡ ወእም ። ወለዝ
ንቱ ፡ ፍትሕ ፡ ኢይገብሩ ፡ ቦቱ ፡ እስመ ፡ አኃው
ይቀርቡ ፡ እምውሉዶሙ ፡ ወቅሩብ ፡ ይቀድሞ ፡
ለዘርኁቅ ።

፩ሺ፫፻፸ ምዕራፍ ፡ ሳብዕ ። ወውስቴቱ ፡ ፪ቱ ፡ መዓር
ጋት ፡ ሳምኒት ፡ ወታስዓት ፡ በአንተ ፡ ዘይወር
ስዎ ፡ እምኔወ ፡ ምዉት ፡ ወእምኅውቱ ፡ ዘአ
ቡሁ ። ወምክንያተ ፡ ቀዲሞቶሙስ ፡ ለእምኔ
ዋን ፡ እምነ ፡ አኃወ ፡ አብ ፡ በአንተ ፡ ዘኮኑ ፡

ስለ ፡ ርስት ።

አንዱ ፡ ሆና ፡ ከሁሉም ፡ ጋራ ፡ ትውረስ ፡
አንጂ ። ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ ወራሽ ፡ ባይገኝ ፡
እኅቱ ፡ በወንድሟ ፡ ስፍራ ፡ ትውረስ ። የወንድ
ሞች ፡ ልጆች ፡ ይከልከሉ ። ከእነዚህ ፡ ወንድ
ሞች ፡ ከአንዱ ፡ ጋራ ፡ እንድትተካከል ፡ መጽ
ሐፍ ፡ ታዝዛለችና ። ወንድምም ፡ ልጆቹን ፡
ይከልክል ። ለአያታቸው ፡ እርሷ ፡ ትቀርባለ
ችና ።

፩ሺ፫፻፷፯ መከ ፡ ፹፰ ። አባት ፡ እናት ፡ ወንድሞች ፡
ከአባት ፡ ወንድሞችና ፡ ከአባት ፡ ወንድሞች ፡
ልጆች ፡ ጋራ ፡ ሦስታቸው ፡ ይካፈሉ ።

፩ሺ፫፻፷፰ ሰባተኛይቱ ፡ መዓርግ ፡ ፍርዱስ ፡ ወደአባት ፡
ለሚቀርበው ፡ ይቀርባል ፡ ባወራረስ ፡ ማመል
ከት ፡ ከልጁ ፡ ቀጥሎ ፡ የልጅ ፡ ልጁ ፡ ከአባትም
ወንድም ፡ ቀጥሎ ፡ የአባት ፡ የወንድም ፡ ልጅ ፡
አወራረስ ፡ ከወንድሞች ፡ ልጆች ፡ ወገን ፡ የሆ
ኑት ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ከወንድሞችና ፡ ከእኅ
ቶች ፡ ቀጥሎው ፡ በትክክል ፡ ይውረሱ ። ስለወን
ድሞች ፡ እንደተጻፈ ። ፍጹማን ፡ ካልሆኑት ፡
ከአንድ ፡ እባትና ፡ ከእንዲት ፡ እናት ፡ የተወለ
ዱት ፡ የፍጹማን ፡ ልጆች ፡ ቅድምና ፡ ከእ
ናት ፡ ብቻ ፡ ከተወለዱትም ፡ ከአባት ፡ ብቻ ፡
የተወለዱትን ፡ ማስቀደም ፡ ታወቀ ። ከእነር
ሱም ፡ ቀጥለው ፡ ስለ ፡ ወንድሞች ፡ ልጆች ፡
የሚያስረዳ ፡ ተጽፏል ።

፩ሺ፫፻፷፱ ሥርዋጽ ፡ ጠስ ፡ ፴ ። ለሞተው ፡ ሰው ፡ ከአባ
ቱና ፡ ከእናቱ ፡ የተወለደ ፡ እነሆ ፡ ከእርሱ ፡
አስቀድሞ ፡ የሞተ ፡ ወንድም ፡ ቢኖረው ፡ ልጆ
ችም ፡ ቢኖሩት ፡ እነርሱ ፡ ከአባታቸው ፡ ወንድ
ሞች ፡ ጋር ፡ ይውረሱ ። እነርሱም ፡ ከአባቱና ፡
ከእናቱ ፡ የተወለዱ ፡ የሟች ፡ ወንድሞች ፡
ናቸው ። በአባታቸው ፡ ዕጣ ፡ ይግቡ ። አባታ
ቸው ፡ በሕይወቱ ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡ ይገባው ፡ የነ
በረውን ፡ ይውሰዱ ። ከአባትና ፡ ከእናት ፡ ካልተ
ወለዱ ፡ ወንድሞች ፡ ያስቀድሟቸው ። በዚህ ፡
ፍርድ ፡ አይሠሩበትም ። ከልጆቻቸው ፡ ወንድ
ሞች ፡ ይቀርባሉና ። የራቀውንም ፡ የቀረበው ፡
ይቀድመዋልና ።

፩ሺ፫፻፸ ፯ኛ ፡ ምዕራፍ ። በውስጡም ፡ ሁለት ፡ መዓር
ጋት ፡ አሉበት ። ፰ኛዪቱና ፡ ፱ነኛዪቱ ። የሟች
ወንድ ፡ አያትና ፡ በአባቱ ፡ በኩል ፡ የሴት ፡
አያቱ ፡ ስለሚወርሱት ፡ ይናገራል ። ከአባት ፡
ወንድሞች ፡ አያቶች ፡ የሚቀድሙበት ፡ ምክ

አንቀጽ ፡ ፵፪ ።

ቅሩባን ፡ እስመ ፡ ማእከለ ፡ እምኔሁ ፡ ወውሉደ ፡ ውሉድ ፡ ቦ ፡ ክልኤቱ ፡ ልደታት ፡ ወማእከለ ፡ እኁሁ ፡ አብ ፡ ወውሉደ ፡ እኁ ፡ ቦ ፡ ፫ቱ ፡ ልደታት ፡ በከመ ፡ ተጠየቀ ፡ በአንቀጸ ፡ አውሰቦ ፡ እምነ ፡ አብጥሊስ ፡ በእንተ ፡ እምኔሆሙ ፡ አቡሁ ፡ ወእምኔሆሙ ፡ እሙ ፡ እስመ ፡ ዘመደ ፡ አብ ፡ ይቀድም ፡ እምዘመደ ፡ እም ።

፩ሺ፫፻፸ ጠስ ፡ ፴ ፡ ወእመ ፡ ኢሀለዉ ፡ ወራስያን ፡ እለ ፡ ይትኈለቁ ፡ ኀበ ፡ ታሕቱ ፡ እስመ ፡ ልዑላውያን ፡ ይቀድሙ ፡ እምሰብእ ፡ ገበዋት ፡ ቅሩባን ፡ በስፌ ፡ ወለፌ ፡ ዘእንበለ ፡ እለ ፡ ይከውኑ ፡ እኀዊሁ ።

፩ሺ፫፻፸፩ መከ ፡ ፹ወ፰ቱ ፡ እምድኅረ ፡ ተባዕት ፡ ይረሳ ፡ አንስት ፡ ዘእዝማደ ፡ አብ ፡ ወእምድኅሬሆን ፡ ይረሱ ፡ ነገደ ፡ እሙ ፡ እስመ ፡ ተፈልጠ ፡ ዘዘከር ፡ እምነ ፡ እሉ ፡ ፪ቱ ፡ ቀኖናት ፡ ንቡራን ፡ ይበጽሕ ፡ ምግብና ፡ ኀበ ፡ እምኔሆሙ ፡ መዋቲ ፡ ለአቡሁ ፡ እምድኅረ ፡ እኀዊሁ ፡ ወቅድምና ፡ እምኔሆሙ ፡ አቡሁ ፡ ወእምኔሆሙ ፡ እሙ ።

፩ሺ፫፻፸፪ምዕራፍ ፡ ሳምን ። ቦቱ ፡ ፪ቱ ፡ መዓርጋት ፡ ዘ፲ቱ ፡ ዘ፲ወ፩ዱ ፡ በእንተ ፡ ዘይወርስዎ ፡ እኃወ ፡ አቡሁ ፡ ስምዐት ፡ ወውሉደ ፡ እኀወ ፡ አቡሁ ፡ ወዘከመ ፡ ተሠርዐ ፡ ሎሙ ፡ ሥርዓት ፡ ምስለ ፡ እሙ ። ወምክንያተ ፡ ቀዲሞቶሙስ ፡ ለአኃወ ፡ አብ ፡ ወውሉዶሙ ፡ እምነ ፡ እኃት ፡ ወውሉደ ፡ እኃት ፡ እስመ ፡ እሉ ፡ ይወፅኡ ፡ እምነገደ ፡ አብ ፡ ኀበ ፡ ነገደ ፡ ብእሲት ፡ እማቲ ፡ ሆሙ ።

፩ሺ፫፻፸፫ መከ ፡ ፲ወ፱ቱ ፡ ወዘአልቦቱ ፡ ወልድ ፡ እምድኅሬሁ ፡ እው ፡ ወላድያን ፡ ወኢ ፡ እኀው ፡ ወኢ ፡ ወልደ ፡ እኀው ፡ ወኢ ፡ ብእሲት ፡ ይረስዎ ፡ እኃወ ፡ አቡሁ ፡ ወለእመ ፡ አልቦቱ ፡ እኃወ ፡ አብ ፡ ይረስዎ ፡ ውሉደ ፡ እኃወ ፡ አቡሁ ።

፩ሺ፫፻፸፬ መከ ፡ ፳ወ፰ቱ ፡ እኃወ ፡ አቡሁ ፡ ወውሉደ ፡ እኃወ ፡ አቡሁ ፡ ምስለ ፡ እሙ ፡ ፫ቲሆሙ ፡ ይትካፈሉ ፡ ሣልስተ ፡ እድ ፡ ወላቲ ፡ ሣልስተ ፡ እድ ፡ ፪ቱ ፡ ወለእመ ፡ አልቦቱ ፡ እኁሁ ፡ ወኢ ፡ ወልደ ፡ እኁሁ ፡ እስመ ፡ ርስት ፡ ትከውን ፡ ለአለ ፡ ተርፉ ፡ እምነ ፡ ኵሉ ፡ ዘመድ ፡ ዘለፌ ፡

ስለ ፡ ርስት ።

ንያት ፡ የሚቀርቡ ፡ ስለሆኑ ፡ ነው ። በእያትና ፡ በልጅ ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ሁለት ፡ ልደት ፡ አለና ። በአባት ፡ ወንድምና ፡ በወንድም ፡ ልጆችም ፡ መካከል ፡ ሦስት ፡ ልደት ፡ አለና በአባቱ ፡ በኩል ፡ ስላለ ፡ አያትና ፡ በእናት ፡ በኩል ፡ ስላለ ፡ አያት ፡ በጋብቻ ፡ አንቀጽ ፡ እንተነገረ ። ከእናት ፡ ዘመድ ፡ የአባት ፡ ዘመድ ፡ ይቀድማልና ።

፩ሺ፫፻፸ ጠስ ፡ ፴ ። ወደታች ፡ የሚቆጠሩ ፡ ወራሾች ፡ ከሌሉ ፡ ወንድሞቹ ፡ ካልሆኑ ፡ በቀር ፡ በጎንና ፡ በጎን ፡ ቀራቢዎች ፡ ከሆኑ ፡ ከጎን ፡ ሰዎች ፡ ወደ ላይ ፡ ያሉ ፡ ይቀድማሉና ።

፩ሺ፫፻፸፩ መከ ፡ ፹፰ ። ከወንዶች ፡ ቀጥለው ፡ በአባት ፡ ዘመዶች ፡ ወገን ፡ ያሉ ፡ ሴቶች ፡ ይውረሱ ። ከእነርሱም ፡ ቀጥለው ፡ የእናት ፡ ወገኖች ፡ ይውረሱ ። ከእኒህ ፡ ከተጠቀሱት ፡ ከሁለቱ ፡ መጻሕፍት ፡ የተጠቀሰው ፡ መለየትስ ፡ ከወንድሞቹ ፡ ቀጥሎ ፡ በአባቱ ፡ በኩል ፡ ወደአለ ፡ የሚች ፡ አያት ፡ አስተዳደር ፡ ስለሚደርስ ፡ ነው ። በአባቱ ፡ በኩል ፡ ያለ ፡ ያያቱና ፡ በእናቱ ፡ በኩል ፡ ያለ ፡ ያያቱ ፡ መቀዳደም ፡ ስለሚሆን ፡ ነው ።

፩ሺ፫፻፸፪ ስምንተኛ ፡ ምዕራፍ ። ሁለት ፡ መዓርጋት ፡ አሉበት ። አሥረኛዪቱና ፡ አሥራ ፡ አንደኛዪቱ የሚች ፡ የአባት ፡ ወንድሞችና ፡ የአባቱ ፡ የወንድሞች ፡ ልጆች ፡ ስለሚወርሱት ፡ ይናገራል ። ከእናቱ ፡ ጋራ ፡ ሥርዓት ፡ እንደተሠራላቸው ፡ የአባት ፡ ወንድሞችና ፡ ልጆቻቸው ፡ ከእኅቶችና ከእኅቶች ፡ ልጆች ፡ የመቅደማቸው ፡ ምክንያት እነርሱ ፡ ከአባት ፡ ወገን ፡ ወደእናት ፡ ወገን ፡ እናቶቻቸው ፡ ስለሚወጡ ፡ ነው ።

፩ሺ፫፻፸፫ መከ ፡ ፲፱ ። ከእርሱ ፡ ቀጥሎ ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ ወላጆች ፡ ወይም ፡ ወንድሞች ፡ ወይም ፡ የወንድም ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ ሚስት ፡ የሌለውን ፡ ሰው የአባቱ ፡ ወንድሞች ፡ ይውረሱት ። የአባት ፡ ወንድሞች ፡ ባይኖሩት ፡ የአባቱ ፡ የወንድሞች፡ ልጆች ፡ ይውረሱት ።

፩ሺ፫፻፸፬ መከ ፡ ፳፰ ። የአባቱ ፡ ወንድሞችና ፡ የአባቱ የወንድሞቹ ፡ ልጆች ፡ ከእናቱ ፡ ጋራ ፡ ሦስቱ ቸው ፡ ሦስት ፡ ልጅ ፡ ይካፈሉ ። ከሦስቱ ፡ እጅ፡ ሁለቱ ፡ ለአርሷ ፡ ይሁን ። ወንድም ፡ ወይም ፡ የወንድም ፡ ልጅ ፡ ባይኖረው ፡ ርስት ፡ በወዲያና ፡ በወዲህ ፡ ካሉ ፡ ዘመዶች ፡ ሁሉ ፡ ለቀሩት፡

ወለፊ ። ጠስ ፡ ፴ ፡ በበመዓርግ ፡ ቅሩባን ፡ ወለ እመ ፡ ተረክበ ፡ በ፩ዱሂ ፡ እምነ ፡ ነቲሉ ፡ መዓ ርግ ፡ እሙንቱ ፡ ይረስ ፡ በዕሩና ።

፩ሺ፫፻፸፭ ምዕራፍ ፡ ሣልስ ፡ ወበ ፡ ውስቴቱ ፡ ፪ቱ ፡ መዓርጋት ፡ ዘ፲ወ፪ቱ ፡ ዘ፲ወ፫ቱ ፡ ዘከመ ፡ ይወ ርስ ፡ ውሉደ ፡ አዋልዲሁ ፡ ወውሉደ ፡ አኃ ቲሁ ፡ ለምዉት ። መከ ፡ ዘ፲ወ፰ቱ ፡ ወለእመ ፡ አልቦቱ ፡ አኃው ፡ ወኢውሉደ ፡ አኃው ፡ ወኢ አኃወ ፡ አብ ፡ ወኢውሉደ ፡ አኃወ ፡ አብ ፡ አሜሃ ይረስዎ ፡ ውሉደ ፡ አዋልዲሁ ፡ ወለእመ ፡ አል ቦን ፡ ለአዋልዲሁ ፡ ውሉድ ፡ ወረሰዮን ፡ ይረ ስዎ ፡ ውሉደ ፡ አኃቲሁ ።

፩ሺ፫፻፸፮ ምዕራፍ ፡ ዓሥር ። ወውስቴቱ ፡ ተረፈ ፡ መዓርጋት ። መከ ፡ ፲ወ፩ዱ ፡ ወለእመሰ ፡ አል ቦቱ ፡ ለመዋቲ ፡ ወልድ ፡ ወኢ ፡ ወላድያን ፡ ወኢ ፡ አኃው ፡ ወኢ ፡ ወልደ ፡ አኃው ፡ ወኢ ፡ ወልደ ፡ እኅት ፡ ይረሳሁ ፡ እንከ ፡ አኃተ ፡ አቡሁ ወእመሰ ፡ ኢሀለዋ ፡ አኃተ ፡ አቡሁ ፡ ይረስዎ ፡ ደቂቆን ፡ ወዛቲ ፡ መዓርግ ፡ ቀዳሚት ፡ ዘባቲ ፡ ይትዔረዩ ፡ ደቂቅ ፡ ምስለ ፡ አዋልድ ፡ ወእሙ ንቱ ፡ ውሉዱ ፡ ለብእሲ ፡ ወበመዓርግሰ ፡ ዳግ ሚት ፡ ወዘእምድኅሬሃ ፡ ኢይወርሳ ፡ አንስት ፡ ወውሉዶን ፡ ምስለ ፡ አኃዊሆን ፡ ወኢምስለ ፡ ውሉደ ፡ አኃዊሆን ።

፩ሺ፫፻፸፯ መከ ፡ ፲ወ፫ቱ ፡ ወተዋርሶሰ ፡ ይትከላእ ፡ እምአንስት ፡ እምድኅረ ፡ መዓርግ ፡ ቀዳማዊ ፡ ወኢይረስ ፡ ውሉደ ፡ አንስት ፡ ምስለ ፡ ውሉደ ፡ ተባዕት ፡ ወኢይረስ ፡ ውሉደ ፡ አኃት ፡ ምስለ ፡ ውሉደ ፡ አኃው ፡ ወኢ ፡ ውሉደ ፡ አኃተ ፡ አብ ፡ ምስለ ፡ ውሉደ ፡ አኃወ ፡ አብ ፡ ወኢውሉደ ፡ አኃተ ፡ እም ፡ ምስለ ፡ ውሉደ ፡ አኃወ ፡ እም ።

፩ሺ፫፻፸፰ ወለእመ ፡ ተፈጸመ ፡ ዘርአ ፡ አቡሆሙ ፡ እምተባዕት ፡ ያእቲ ፡ ጊዜ ፡ ይረስ ፡ አዝርእ ቲሁ ፡ እለ ፡ ተወልዱ ፡ እምአንስት ፡ ወእመሂ ፡ ኀልቁ ፡ አዝርእቲሁ ፡ እለ ፡ እምአንስት ፡ ያእቲ ጊዜ ፡ ይረስ ፡ ዘርአ ፡ ለእም ።

፩ሺ፫፻፸፱ ወበከመ ፡ ዘከሩ ፡ በዙንኤያተ ፡ ፍትሕ ፡ ይረስ ፡ እምድኅረ ፡ አኃተ ፡ አብ ፡ ዘመዳ ፡ ለእም ፡ ዘውእቱ ፡ አቡሃ ፡ ለእመ ፡ ምዉት ፡



ትሆናለች ። ጠስ ፡ ፴ ። በየመዓርግ ፡ የተቀ ራረቡ ፡ ዘመዶች ፡ ከመዓርግ ፡ ሁሉ ፡ በአንዱ ፡ ቢገኙ ፡ እነርሱ ፡ በትክክል ፡ ይወረሱ ።

፩ሺ፫፻፸፭ ፱ኛ ፡ ምዕራፍ ። በውስጡ ፡ ሁለት ፡ መዓር ጋት ፡ አሉ ። ፲፪ኛና ፡ ፲፫ኛ ። የሚቹ ፡ የሴት ፡ ልጆቹ ፡ ልጆችና ፡ የእኅቶቹ ፡ ልጆች ፡ እንደሚ ወርሱ ፡ ይናገራል ። መከ ፡ ፲፪ ። ወንድሞች ፡ ወይም ፡ የወንድሞች ፡ ልጆች ፡ ወይም ፡ የአባት ወንድሞች ፡ ወይም ፡ የአባት ፡ የወንድሞች ፡ ልጆች ፡ ባይኖሩት ፡ ያንጊዜ ፡ የሴቶች ፡ ልጆቹ ፡ ልጆች ፡ ይውረሱት ። ለሴቶች ፡ ልጆቹ ፡ ወራ ሾች ፡ ልጆች ፡ ባይኖሯቸው ፡ የእኅቶች ፡ ልጆች ፡ ይውረሱት ።

፩ሺ፫፻፸፮ ፲ኛ ፡ ምዕራፍ በውስጡ የመዓርጋት ትርፍ አለበት ። መከ ፲፩ ። ለሚች ልጅ ፡ ወይም ፡ ወላጆች ፡ ወይም ፡ ወንድሞች ፡ ወይም የወንድም ልጆች ፡ ወይም ፡ የእኅት ልጅ ባይኖሩት ፡ እንግዲህ ፡ የአባቱ ፡ እኅቶች ፡ (አክ ስቶች) ፡ ይውረሱት ። የአባቱ ፡ እኅቶች ፡ ባይኖሩትም ፡ ልጆቻቸው ፡ ይውረሱት ። ወንዶች ልጆች ከሴቶች ልጆች ጋራ የሚተካከሉባት ፡ አንደኛ መዓርግ ይች ናት ። እነርሱም የሰውየው (የሚቹ) ልጆች ናቸው ። በሁለተኛዪቱና ፡ ከእርሷም ቀጥላ በአለችው ፡ መዓርግ ፡ ግን ሴቶችና ልጆቻ ቸው ፡ ከወንድሞቻቸውና ፡ ከወንድሞቻቸው ልጆች ፡ ጋራ ፡ አይወርሱም ።

፩ሺ፫፻፸፯ መከ ፡ ፲፫ ። መውረስስ ፡ ከመጀመሪያው ፡ መዓርግ ፡ በኋላ ፡ ከሴቶች ፡ ይከለከላል ። የሴ ቶች ፡ ልጆች ፡ ከወንዶች ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ አይ ወርሱም ። የእኅቶች ፡ ልጆችም ፡ ከወንድሞች ልጆች ፡ ጋራ ፡ የአባት ፡ የእኅቶች ፡ ልጆችም ከአባት ፡ የወንድሞች ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ የእናት የእኅቶች ፡ ልጆችም ፡ ከእናት ፡ የወንድሞች ልጆች ፡ ጋራ ፡ አይወረሱ ።

፩ሺ፫፻፸፰ ከወንድ ፡ ወገን ፡ የአባታቸው ፡ ዘር ቢያ ልቅ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ከሴቶች ፡ የተወለዱ ፡ ልጆቹ ይውረሱ ፡ ከሴቶች ፡ ወገን ፡ ያሉት ፡ ልጆች ቢያልቁ ፡ ያንጊዜ ፡ የእናት ፡ ልጆች ፡ ይውረሱ ።

፩ሺ፫፻፸፱ በፍርድ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ተናገሩ ፡ ከአባት ፡ እኅቶች ፡ ቀጥለው ፡ የእናት ፡ ዘመዶች ፡ ይው ረሱ ። ይኸውም ፡ የሚቹ ፡ እናት ፡ አባቷ ፡ ነው።

አንቀጽ ፡ ፵፱ ።

ወእምድኅሬሁ ፡ እመ ፡ እሙ ፡ ወድኅሬሃ ፡ እኅወ ፡ እሙ ፡ እስመ ፡ ማእከለ ፡ ምዉት ፡ ወማእከለ ፡ እምኄው ፡ ፪ቱ ፡ ልደታት ፡ ወማእከሌሁ ፡ ወማእከለ ፡ እኅወ ፡ እሙ ፡ ፫ቱ ፡ ልደታት ። ወእምድኅረ ፡ እኅወ ፡ እም ፡ ውሉደ ፡ እኅወ ፡ እም ፡ ተባዕት ፡ ወአንስት ፡ በከመ ፡ ገብሩ ፡ በሥርዓተ ፡ ውሉደ ፡ እኅወ ፡ አብ እምድኅረ ፡ እኅወ ፡ አብ ፡ ወእምድኅረ ፡ ውሉደ እኃወ ፡ እም ፡ እኅታ ፡ ለእመ ፡ ምዉት ፡ ወእምድኅሬሃ ፡ ውሉደ ፡ ዚአሃ ፡ ተባዕት ፡ ወአንስት ፡ ወእምድኅሬሆሙ ፡ አበወ ፡ እምኄዋን ፡ ወእምድኅሬሆሙኒ ፡ በከመ ፡ ቀደመ ፡ ዝክሩ ።

፩ሺ፫፻፺ መጅ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ወዘሰ ፡ አልቦቱ ፡ ዘይወርሶ ፡ ይኩን ፡ ዘኀደገ ፡ ለቤተ ፡ መዝገበ ፡ ንዋይ ።

፩ሺ፫፻፺፩ ምዕራፍ ፡ ፲ወ፩ዱ ። በእንተ ፡ ተዋርሶተ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ወመነኮሳት ። ረስጠጅ ፡ ፴ወ፱ቱ ፡ ወይኩን ፡ ዕዉቀ ፡ ንዋየ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወስይኩን ፡ እሙረ ፡ ንዋየ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ሎቱ ፡ ሥልጣን ፡ ላዕለ ፡ ዘኮነ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ቦቱ ፡ ዘኀለየ ፡ ወያውርሶ ፡ ለዘፈቀደ ፡ ወኢይኅጉል ፡ ንዋዩ ፡ በምክንያተ ፡ ንዋየ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

፩ሺ፫፻፺፪ ወለእመ ፡ ኮኑ ፡ ሎቱ ፡ ለኤጲቆጶስ ፡ አዝማድ ፡ ወውሉድ ፡ ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ገቢረ ፡ ርትዕ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ኢይትኅጎል ፡ ምንትኒ ፡ እምንዋየ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወከመ ፡ ኢየሀቦ ፡ ለዘፈቀደ ፡ ከመ ፡ ይትመነኖብ፡ ቦቱ ፡ ወከመ ፡ ኢየዓምዕዎ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ በንዋየ ፡ ዚአሁ ፡ ወኢይትገአዙ ፡ ሰብአ ፡ ቤቱ ፡ ወእዝማዲሁ ፡ ላዕለ ፡ ዘኮነ ፡ ሎቱ ፡ በተመክንዮተ ፡ ንዋየ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወኢይኩን ፡ ዝንቱ ፡ ዘየመጽእ ፡ ኀፍረተ ፡ ወኀሣረ ወነውረ ፡ እምድኅረ ፡ ሞቱ ፡ ወዝክረ ፡ እኩየ ። ጠስ ፡ ፴ወ፩ዱ ፡ ወከመ ፡ ኢይደቁ ፡ አዝማዲሁ፡ ውስተ ፡ ጻማ ፡ ወኢይሰርፉ ፡ ላዕሌሁ ።

፩ሺ፫፻፺፫ ጠስ ፡ ፳ወ፱ቱ ፡ ወኵሎ ፡ ዘአጥረየ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እምቅድመ ፡ ይሠየም ፡ ኤጲስቆጶስና ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ የሀብ ፡ ለዘፈቀደ ፡ ከመ ፡ ይትመነኖብ ፡ ቦቱ ፡ ወየእገዝዝ ፡ ቦቱ ። ወዘአጥረየሰ ፡ እምድኅረ ፡ ኤጲስቆጶስናሁ ፡ ይኩን ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወኢይደልዎ ፡ ሎቱ ፡ ትእዛዝ ፡

ስለ ፡ ርስት ።

ከእርሱ ፡ ቀጥሎ ፡ የእናቱ ፡ እናት ፡ ከእርሷ ፡ ቀጥሎም ፡ የእናቱ ፡ ወንድም ፡ በሚቹና ፡ ባያቱ መካከል ፡ ሁለት ፡ ልደቶች ፡ አሉና ፡ በእርሱና ፡ በእናቱ ፡ ወንድም ፡ መካከል ፡ ሦስት ፡ ልደት ፡ አለና ። ከእናት ፡ ወንድም ፡ ቀጥሎ ፡ የእናት ፡ የወንድም ፡ ልጆች ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ከአባት ፡ ወንድም ፡ ተጥሎ ፡ በአባት ፡ የወንድም ልጆች ፡ ሥርዓት ፡ እንዳደረጉ ፡ ከእናት ፡ የወንድሞች ፡ ልጆች ፡ ቀጥሎ ፡ የሚቹ ፡ የእናቱ ፡ እኅት ፡ ከርሷም ፡ ቀጥለው ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ልጆች ፡ ከእነርሱም ፡ ቀጥለው ፡ የያቶቻቸው ፡ አባቶች ፡ ከእነርሱም ፡ ቀጥሎ ፡ አስቀድሞ ፡ እንደተነገረው ፡ ይሁን ።

፩ሺ፫፻፺ መጅ ፡ ፲፪ ። ወራሽ ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ የተወው ገንዘቡ ፡ ለገንዘብ ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ይሁን ።

፩ሺ፫፻፺፩ ፲፩ኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ስለ ፡ ኤጲስቆጶሳትና ፡ ስለ ፡ መነኮሳት ፡ አወራረስ ፡ ይናገራል ። ረስጠጅ ፡ ፴፱ ፡ የኤጲስቆጶሱ ፡ ገንዘብ ፡ የታወቀ ፡ ይሁን ። የቤተ ፡ ክርስቲያኑም ፡ ገንዘብ ፡ የታወቀ ፡ ይሁን ። የወደደውን ፡ ሊያደርግበት ፡ ለእርሱ ፡ በሆነው ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ይኖረው ፡ ዘንድ ፡ ለወደደውም ፡ ያወርሰው ፡ ዘንድ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኑም ፡ ገንዘብ ፡ ምክንያት ፡ ገንዘቡ ፡ እንዳይጠፋበት ።

፩ሺ፫፻፺፪ ለኤጲስቆጶሱ ፡ ዘመዶችና ፡ ልጆች ፡ ቢኖሩት ፡ የሚገባ ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይህ ፡ ነው ። ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገንዘብ እንዳችም ፡ እንዳይጠፋ ። ይበላውም ፡ ዘንድ ፡ ለወደደው ፡ እንዳይሰጠው ። ኤጲስቆጶሱንም ፡ በገንዘቡ ፡ እንዳይበድሉት ። ቤተ ፡ ሰቦቹና ፡ ዘመዶቹ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገንዘብ ፡ በማመካኘት ፡ ለእርሱ ፡ በሆነው ፡ ላይ ፡ እንዳይከራከሩ ይህም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ኃፍረትን ፡ ውርደትን ፡ ነቀፋን ፡ ክፉ ፡ ስም ፡ አጠራርን ፡ የሚያመጣ ፡ እንዳይሆን ። ጠስ ፡ ፴፩ ፡ ዘመዶቹም ፡ በችጋር ፡ ላይ ፡ እንዳይወድቁና ፡ እርሱን ፡ እንዳይረግሙት ።

፩ሺ፫፻፺፫ ጠስ ፡ ፳፱ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ኤጲስቆጶስነት ከመሾሙ ፡ አስቀድሞ ፡ ያጠራቀመውን ፡ ገንዘብ ፡ ያስተዳድርበትና ፡ ያዝዝበት ፡ ዘንድ ፡ ለወደደው ፡ ሊሰጥ ፡ ይገባዋል ። ከኤጲስ ቆላጶስነቱ ፡ በኋላ ፡ ያጠራቀመው ፡ ገንዘብ ፡ ግን ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይሁን ። ከእርሱ ፡ በምንም

አንቀጽ ፡ ፵፪ ።

ከመ ፡ የአገዝዝ ፡ በምንትኒ ፡ እምኔሁ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘእምጽኡ ፡ ሎቱ ፡ እምርስት ፡ ዘወላድያኒሁ ፡ ወእኅዊሁ ፡ አው ፡ ዘአኃው ፡ አቡሁ ።

፩ሺ፫፻፶፬ በስ ፡ ፵ ፤ እምከመ ፡ ተሠይመ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እንዘ ፡ ነዳይ ፡ ውእቱ ፤ ወእምዝ ፡ አጥረየ ፡ ብዕለ ፡ እምድኅረ ፡ ሢመቱ ፡ ተዐውቀ ፡ ከመ ፡ ዘአጥረዮ ፡ እምንዋየ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውእቱ ፡ ወይኩን ፡ እምድኅረ ፡ ሞቱ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ። ወባሕቱ ፡ ውሉዱ ፡ ኢይኅጥኡ ፡ ዘይትወሀብ ፡ ሎሙ ፡ እምንዋየ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በእንተ ፡ ዘኢኮኑ ፡ ድልዋነ ፡ እምንዋየ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ። ወፈድፋደስ ፡ እመ ፡ ሀለዉ ፡ ሎቱ ፡ አዝማድ ፡ ጽኑሳን ፡ የሀብዎሙ ፡ ሲሳዮሙ ፡ እምንዋየ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

፩ሺ፫፻፶፭ ጠስ ፡ ፰ወ፬ቱ ፡ ወዘመንኰሰ ፡ እንዘ ፡ ቦቱ ፡ ውሉድ ፡ ይደልዎ ፡ ሎቱ ፡ እምድኅረ ፡ ምንኵስናሁ ፡ ከመ ፡ ይክፍል ፡ ኵሎ ፡ ንዋዮ ፡ ለውሉዱ ፤ እምድኅረ ፡ ከፈለ ፡ ለነፍሱ ፡ ፩ደ ፡ ክፍለ፡ ዘይከውን ፡ ለምኔት ። ወለእመሰ ፡ ሞተ ፡ ዘእንበለ ፡ ይጽሐፍ ፡ ትእዛዘ ፡ ይንሥኡ ፡ ውሉዱ ፡ አሜሃ ፡ ዘይደልዎሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ጽሒፈ ፡ ትእዛዝ ፤ ወእሙንቱስ ፡ ይሰመዩ ፡ ወራስያነ ፡ ወውእቱ ፡ ይሰመይ ፡ ፈልክዶነ ፡ ወለዘተርፈስ ፡ የሀብዎ ፡ ለምኔት ። ወለእመሰ ፡ አልቦቱ ፡ ውሉድ ፡ ወኢያብእ ፡ ንዋዮ ፡ ውበተ ፡ ምኔት ፡ መላኪ ፡ ውእቱ ፡ በትእዛዙ ። ወእመሰ ፡ አብአ ፡ ንዋዮ ፡ ውስተ ፡ ምኔት ፡ ወእመ ፡ ይቤ ፡ ውእቱ ፡ ይባእ ፡ ንዋይየ ፡ ውስተ ፡ ምኔት ፡ ይኩን ፡ ንዋዩ ፡ ለምኔት ፡ በከመ ፡ አዘዘ ፡ ውእቱ ፡ ቅድመ ፡ በዊአቱ፡ ውስተ ፡ ምኔት ።

፩ሺ፫፻፶፮ ምዕራፍ ፡ ፲ወ፪ቱ ። በእንተ ፡ አግብርት ፡ ወግዑዛን ፤ ኢይረስ ፡ ገብር ፡ ዘእንበለ ፡ በትእዛዘ ፡ ዘያወርሶ ፡ እስመ ፡ ርስትሰ ፡ ለአዝማድ ፡ ወለውእቱኒ ፡ ኢይረስዎ ፡ ዘእንበለ ፡ እግዚኡ ፡ እስመ ፡ ንዋይ ፡ ዘእግዚኡ ፡ ውእቱ ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ኢይከውን ፡ አማነ ፡ ትእዛዙ ፡ ወኢ ሠይጦቱ ፡ ዘእንበለ ፡ በመባሕተ ፡ እግዚኡ ።

፩ሺ፫፻፶፯ መክ ፡ ፵ወ፫ቱ ፡ ወለእመ ፡ ፈቀደ ፡ ገብር ፡ እምድኅረ ፡ ግዕዛኑ ፡ ከመ ፡ ያውስብ ፡ አመተ ፡ ወወለደ ፡ እምኔሃ ፡ ውሉደ ፡ እስመ ፡ ሕግነ ፡ ትኤዝዝ ፡ ከመ ፡ ኢይረሶ ፡ ወልዱ ፡ ዘእምአ

ስለ ፡ ርስት ።

ያዝዝ ፡ ዘንድ ፡ ለእርሱ ፡ ትእዛዝ ፡ አይገባውም ። ከወላጆቹና ፡ ከወንድሞቹ ፡ ወይም ፡ ከአባቶቹ ፡ ወንድሞች ፡ ርስት ፡ ካመጡለት ፡ ገንዘብ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ።

፩ሺ፫፻፶፬ በስ ፡ ፵ ። ኤጲስቆጶስ ፡ ደኅ ፡ ሳለ ፡ ቢሾም ፡ ከሹመቱ ፡ በኋላ ፡ ሀብት ፡ ቢያበጅ ፡ የሰበሰበውን ፡ ገንዘብ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገንዘብ ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ ታወቀ ። ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይሁን ። ነገር ፡ ግን ፤ ልጆቹ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገንዘብ ፡ የሚገባቸው ፤ ስላልሆኑ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገንዘብ ፡ የሚሰጧቸውን ፡ አይከልክሉ ። ይልቁንም ፡ ችግረኞች ፡ ዘመዶች ፡ ቢኖሩት ፡ ምግባቸውን ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገንዘብ ፡ ይስጧቸው ።

፩ሺ፫፻፶፭ ጠስ ፡ ፰፬ ። ልጆች ፡ እያሉት ፡ የመነኰሰ ከምንኵስናው ፡ በኋላ ፡ ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ ለልጆቹ ፡ ሊያካፍል ፡ ይገባዋል ። ለገዳሙ ፡ የሚሆን ለእራሱ ፡ አንድ ፡ ዕጣ ፡ ከከፈለ ፡ በኋላ ፡ ትእዙን ፡ ሳይጽፍ ፡ ቢሞት ፡ ግን ፡ ያንጊዜ ፡ ልጆቹ ፡ ያለትእዛዝ ፡ ጽሕፈት ፡ የሚገባቸውን ፡ ይውሰዱ ። እነርሱም ፡ ወራሾች ፡ ይባላሉ ፡ እርሱም ፡ አውራሽ ፡ ይባላል ። የቀረውን ፡ ግን ፡ ለገዳሙ ፡ ይስጡት ። ልጆች ፡ ባይኖሩት ፡ ገንዘቡንም ፡ ለገዳሙ ፡ ቢያገባ ፡ ግን ፡ እርሱም ፡ ገንዘቤ ፡ ለገዳሙ ፡ ይግባ ፡ ቢል ፡ ወደ ፡ ገዳም ፡ ከመግባቱ ፡ አስቀድሞ ፡ እርሱ ፡ እንዳዘዘ ፡ ገንዘቡ ፡ ለገዳሙ ፡ ይሁን ።

፩ሺ፫፻፶፮ ፲፪ተኛ ፡ ምዕራፍ ። ነፃ ፡ ስላልወጡ ፡ ባሮችና ፡ ነፃ ፡ ስለወጡ ፡ ባሮች ፡ ይናገራል ። በሚያወርሰው ፡ ትእዛዝ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ባሪያ ፡ አይውረስ ፤ ርስት ፡ ለዘመድ ፡ ነውና ፡ ርሱንም ፡ ከጌታው ፡ በቀር ፡ ሌሎች ፡ አይውረሱት ። እርሱ ፡ ለጌታው ፡ ገንዘብ ፡ ነውና ። ስለዚህ ፡ ያለጌታው ፡ ፈቃድ ፡ ትእዛዙ ፤ መሸጡም ፡ እውነት ፡ አይሆንም ።

፩ሺ፫፻፶፯ መክ ፡ ፵፫ ። ባሪያ ፡ ከነፃነቱ ፡ በኋላ ፡ ነፃ ፡ ያልወጣች ፡ ባሪያ ፡ ሊያገባ ፡ ቢወድ ፡ ከእርሲም ፡ ልጆች ፡ ቢወልድ ፡ ነፃ ፡ ካልወጣችው ፡ ባሪያ ፡ የተወለደው ፡ ልጅ ፡ እንዳይወርሰው

አንቀጽ ፡ ፵፪ ።

መት ፡ እላ ፡ ይኩን ፡ ንዋዩ ፡ ለእግዚኡ ፡ ዘእግዓዝ ።

፩ሺ፫፻፹፰ መጅ ፡ ፰ወ፩ቱ ፡ ወከማሁ ፡ ወልደ ፡ አግዓዚት ፡ ዘተወልደ ፡ እምገብር ፡ ኢይረሳ ፡ ወባሕቱ ፡ ይወርሳ ፡ ዘይደልዎ ፡ ወረሰታ ፡ እምነ ፡ አግዓዝያን ፡ ወለምታኒ ፡ ዘይደልዎ ፡ ክፍሉ ።

፩ሺ፫፻፹፱ መክ ፡ ፲ወ፮ቱ ፡ ጠስ ፡ ፴ ፡ ወኢይደሉ ፡ ለገብር ፡ ከመ ፡ ይጽሐፉ ፡ ሎቱ ፡ ተዋርሶተ ፡ እግዚኡ ፡ ሎቱ ፡ እስመ ፡ ገብር ፡ ንዋይ ፡ ውእቱ ፡ ሶእግዚኡ ፡ በውስተ ፡ ትእዛዝ ።

፩ሺ፫፻፺ ጠስ ፡ ፴ወ፩ቱ ፡ ወእመቦ ፡ ዘኅደገ ፡ ርስተ ፡ ዘፈለሰ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ ዘንዋየ ፡ ንጉሥ ፡ እምንዋየ ፡ ብእሲ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ዘይወርሶ ፡ ወኮኑ ፡ ውስቴቱ ፡ አግብርት ፡ ያግዕዝዎሙ ፡ በጊዜሃ ፡ ወይኩኑ ፡ ግዑዛነ ፡ ወእመኒ ፡ ኮነ ፡ ዙሉ ፡ ዘኅደገ ፡ አግብርተ ፡ እሙንቱ ፡ ያግዕዝዎሙ ። ወዘተዐደወ ፡ ዘንተ ፡ ትእዛዘ ፡ ኢይረክብ ፡ ግዕዛነ ፡ እምኅጣውኢሁ ።

፩ሺ፫፻፺፩ ወዘተግዕዘሰ ፡ ይኩን ፡ ተዋርሶተ ፡ ንዋዩ ፡ በሥርዓተ ፡ ፍትሕ ፡ ዘከዋነ ፡ ተዋርሶ ፡ በውስተ ፡ አብጥሊሳት ፡ ዘ፰ ፡ ወ፫ቱ ፡ ወዘይመስሎ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ይቀውም ፡ ሎቱ ፡ ጽሒፈ ፡ ትእዛዝ ። ወእመኒ ፡ ኮነ ፡ ሎቱ ፡ ወራሲ ፡ ለሊሁ ፡ ይወርስ ፡ ወእመሰ ፡ አልቦቱ ፡ ወራሲ ፡ ወኮነ ፡ ዘእዘዘ ፡ ለካልእ ፡ እምነ ፡ ዘእግዐዞ ፡ ይኩን ፡ ሣልስተ ፡ እድ ፡ ለዘአግዐዞ ። ወእመኒ ፡ ኮነ ፡ በዘየሐጽጽ ፡ እምሣልስተ ፡ እድ ፡ ይኩን ፡ ዘተርፈ ፡ ለዘአግዐዞ ። ወእመሰ ፡ ኢአዘዘ ፡ ግሙራ ፡ ይኩን ፡ ኵሉ ፡ ወረሰ ፡ ንዋዩ ፡ ለዘአግዐዞ ፡ ወእመኒ ፡ ኮነ ፡ ዘግዑዝ ፡ ፩ዱ ፡ ውእቱ ፡ አው ፡ ዘይበዝኅ ፡ እም፩ዱ ፡ ወእምዝ ፡ ይረስዎ ፡ ወራስያኒሁ ፡ ለዘአግዐዞ ፡ እምድኅሬሁ ፡ በአምጣነ ፡ ዘይወርሱ ፡ እምኔሁ ።

፩ሺ፫፻፺፪ መክ ፡ ፰ወ፩ቱ ፡ ወዘጸሐፈ ፡ ለገብሩ ፡ መጽሐፈ ፡ ግዕዛን ፡ ወአበየነ ፡ ምስለ ፡ ርእሱ ፡ ወምስለ ፡ ንዋዩ ፡ ግዑዝ ፡ ውእቱ ። ወለእመሰ ፡ ኢጸሐፈ ፡ ዝከረ ፡ ንዋዩ ፡ ምስለ ፡ ግዕዛን ፡ ዚአሁ ፡ ባሕቲቱ ፡ ሶበ ፡ እግዐዞ ፡ ርእሶ ፡ ባሕቲቶ ፡ ይደልዎሙ ፡ ለወራስያኒሁ ፡ ከመ ፡ ይረሱ ፡ ንዋዮ ።

፩ሺ፫፻፺፫ ምዕራፍ ፡ ፲ወ፫ቱ ። በእንተ ፡ ዘኢይወርሱ ፡ ወዘኢያወርስዎሙሂ ። እለ ፡ ኢይወርሱስ ፡ ዘእ

ስለ ፡ ርስት ።

ሕጋችን ፡ ታዛለችና ፡ (ገላ ፡ ፬ ፡ ፴) ። ገንዘቡ ፡ ነፃ ፡ ላወጣው ፡ ለጌታው ፡ ይሁን ፡ እንጂ ።

፩ሺ፫፻፹፰ መጅ ፡ ፰፩ ። እንደዚኹውም ፡ ነፃ ፡ ካልወጣው ፡ ባሪያ ፡ የተወለደ ፡ ነፃ ፡ የወጣች ፡ የባሪያ ፡ ልጅ ፡ አይውረሳት ። ከጌቶቹ ፡ ወገን ፡ ሊወርሳት ፡ የሚገባው ፡ ይወርሳታል ፡ እንጂ ። የባሏንም ፡ ድርሻ ፡ የሚገባው ፡ ይውረሰው ።

፩ሺ፫፻፹፱ መክ ፡ ፲፮ ፡ ጠስ ፡ ፴ ። ለባሪያ ፡ የጌታውን ፡ መውረስ ፡ ሊጽፉለት ፡ አይገባም ። በሕግ ፡ ባሪያ ፡ ለጌታው ፡ ገንዘብ ፡ ነውና ።

፩ሺ፫፻፺ ጠስ ፡ ፴፩ ። ወራሽ ፡ ከሌለው ፡ ሰው ፡ ገንዘብ ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ዕቃ ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ የተዛወረ ፡ ርስትን ፡ የተወ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ በውስጡም ፡ ባሮች ፡ ቢኖሩበት ፡ ወዲያውኑ ፡ ነፃ ፡ ያውጧቸው ። ነፃም ፡ የወጡ ፡ ይሁኑ ። ከተወዉም ፡ ሀብት ፡ ውስጥ ፡ ባሮች ፡ ቢኖሩ ፡ ነፃ ፡ ያውጧቸው ። ይህን ፡ ትእዛዝ ፡ የተላለፈ ፡ ከኀጢአት ፡ ነፃነትን ፡ አያገኝም ።

፩ሺ፫፻፺፩ ነፃ ፡ የወጣው ፡ ግን ፡ በአብጥሊስ ፡ ውስጥ ፡ የውርስን ፡ ሁኔታ ፡ የሚያስረዳ ፡ በፍርድ ፡ ሥርዓት ፡ የገንዘቡ ፡ ውርስ ፡ ይሁን ። ፰፫ ። የሚመስለውም ፡ የማዘዣው ፡ ደብዳቤ ፡ እንደሚጸናለት ይናገራል ። ወራሽ ፡ ቢኖረው ፡ እርሱ ፡ ይወርሳል ። ወራሽ ፡ ባይኖረው ፡ ግን ፡ ነፃ ፡ ካወጣው ፡ ከጌታው ፡ ለሌላ ፡ ያዘዘ ፡ ቢሆን ፡ ሦስተኛው ፡ እጅ ፡ ነፃ ፡ ላወጣው ፡ ይሁን ። ከሦስት ፡ እጅ ፡ የሚያንስ ፡ ቢሆንም ፡ የተረፈው ፡ ነፃ ፡ ላወጣው ይሁን ። ፈጽሞ ፡ ባይናዘዝ ፡ ግን ፡ ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ መውረስ ፡ ነፃ ፡ ላወጣው ፡ ይሁን ። ነፃ ፡ ያወጣው ፡ አንድ ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ከአንድ ፡ የሚበዛ ፡ ቢሆን ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከእርሱ ፡ ቀጥሎ ፡ ነፃ ፡ የወጣውን ፡ የሚወርሱት ፡ ከእርሱ በሚወርሱት ፡ ልክ ፡ ይውረሱት ።

፩ሺ፫፻፺፪ መክ ፡ ፰፩ ። ለባሪያው ፡ የነፃነት ፡ ደብዳቤ ፡ የጻፈ ፡ ሰው ፡ ራሱን ፡ ከገንዘቡ ፡ ጋራ ፡ ቢለይ ፡ ነፃ ፡ ነው ። ራሱን ፡ ብቻ ፡ ነፃ ፡ ያውጣው ፡ እንጂ ። ከእርሱ ፡ ነፃነት ፡ ጋራ ፡ የገንዘቡን ፡ ስም ፡ ባይጽፍ ፡ ግን ፡ ወራሾቹ ፡ ገንዘቡን ፡ ሊወርሱት ፡ ይገባቸዋል ።

፩ሺ፫፻፺፫ አሥራ ፡ ሦስተኛ ፡ ምዕራፍ ። ስለማይወርሱና ፡ ስለማይወርሷቸው ፡ ይናገራል ። ያለማ

ንበለ ፡ በጽሒፈ ፡ ትእዛዝ ፡ እሉ ፡ እሙንቱ ፡ ዘእ ልቦ ፡ ማእከሌሆሙ ፡ ወማእከለ ፡ ምዉት ፡ ተዘ ምዶ ፡ ጠባይዓዊ ፡ ኢተዋስቦ ፡ ወእመኒ ፡ ሀሎ ፡ ማእከሌሆሙ ፡ ወማእከሌሁ ፡ ግብረ ፡ ተዘምዶ ፡ ዘተሰናእዎ ፡ እው ፡ ዘሕግ ፡ ዘከመ ፡ ሐፃንያት ፡ ወእጥባውያት ፡ ወዓርከት ፡ ወተሐባይያት ፡ በጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ እው ፡ ዘከመ ፡ ተዋስቦ ፡ ዘከመ ፡ ምተ ፡ እም ፡ ወብእሲተ ፡ እብ ፡ ወእዝ ማደ ፡ ምት ፡ ወእዝማደ ፡ ብእሲት ፡ ወእኅዊሁ ፡ ለወልድ ፡ ወእኅቲሁ ፡ ወእበዊሆሙ ፡ ለእኅው ፡ ወለእኅት ፡ ወብእሲተ ፡ እኅው ፡ ወምታ ፡ ለእ ኅት ፡ ወብእሲታተ ፡ ውሉድ ፡ ወእምታተ ፡ እዋ ልድ ። ወእለሰ ፡ ኢይወርስዎሙ ፡ ሀሎ ፡ በእንቲ እሆሙ ፡ ፪ቱ ፡ ክፍል ።

ዘገር ፡ ደብዳቤ ፡ የማይወርሱስ ፡ እሊህ ፡ ናቸው። በነርሱና ፡ በሟቹ ፡ መካከል ፡ ሥጋዊ ፡ ወይም ፡ የጋብቻ ፡ ተዘምዶ ፡ የሌላቸው ፡ ናቸው ። በእነ ርሱና ፡ በእርሱ ፡ መካከል ፡ የፍቅር ፡ ወይም ፡ የሕግ ፡ ዝምድና ፡ ቢኖር ፡ ይኸውም ፡ እን ደ ፡ ሞግዚቶች ፡ ጡት ፡ እንደሚያጠቡ ፡ እንደ ፡ ወዳጆች ፡ ክርስትና ፡ እንደተናሱ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ጋብቻ ። ይኸውም ፡ እንደ ፡ እናት ፡ ባል ፡ (እንጀራ ፡ እባት) ፡ እንደ ፡ እባት ፡ ሚስት ፡ (እንደ ፡ እንጀራ ፡ እናት) ፡ እንደ ፡ ባል ፡ ዘመ ዶችና ፡ እንደ ፡ ሚስት ፡ ዘመዶች ፡ እንደ ፡ ልጅ ፡ ወንድሞችና ፡ እኅቶች ፡ እንደ ፡ ወንድ ምና ፡ እንደ ፡ እኅት ፡ እባቶች ፡ እንደ ፡ ወንድም ሚስትና ፡ እንደ ፡ እኅት ፡ ባል ፡ እንደ ፡ ወንድ ፡ ልጆች ፡ ሚስቶችና ፡ እንደ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ባሎች ፡ ያሉ ፡ ናቸው ። የማይወርሷቸው ፡ ግን ፡ ስለእነርሱ ፡ ሁለት ፡ ክፍል ፡ እለ ።

፩ሺ፫፻፺፩ ክፍል ፡ ቀዳማዊ ፡ ኢይረስ ፡ ወእመኒ ፡ ተእ ዘዘ ፡ ሎቱ ። ጠስ ፡ ፴ወ፫ቱ ፡ ለምእመን ፡ ኢይ ረሶ ፡ ዘኢኮነ ፡ ምእመነ ፡ ወእመኒ ፡ እዘዘ ፡ ሎቱ ወእምዝ ፡ ወፅአ ፡ እምድኅረ ፡ ትእዛዙ ፡ እምሃይ ማኖት ፡ እምቅድመ ፡ ንሢእቱ ፡ ውእተ ፡ ርስተ፡ ወእመሰ ፡ ተጠየቀ ፡ ተመይጦቱ ፡ ኀበ ፡ ሃይማ ኖት ፡ ርትዕት ፡ ይደልዎ ፡ ክፍለ ፡ ዘእሁ ፡ እም ርስት ። ወእመኒ ፡ ተመይጠ ፡ ኀበ ፡ ሃይማኖት ፡ ካልእ ፡ እምድኅረ ፡ ተካፈለ ፡ ርስተ ፡ ኢይደ ልዎ ፡ ከመ ፡ ይረስ ፡ ወለእመኒ ፡ ተእዘዘ ፡ ሎቱ።

፩ሺ፫፻፺፩ እንደኛው ፡ ክፍል ፡ ቢታዘዝለትም ፡ አይው ረስ ። ጠስ ፡ ፴፫ ። ምንም ፡ ቢያዝዝለት ፡ ያመ ነውን ፡ ያላመነው ፡ አይውረሰው ። ካዘዘለት ፡ በኋላ ፡ ይህን ፡ ርስት ፡ ከመቀበሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ከሃይማኖት ፡ ቢወጣ ፡ አይውረስ ። ወደቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ መመለሱ፡ ቢታወቅ ፡ ግን ፡ ክርስቱ ድርሻው ፡ ይገባዋል ። ርስቱን ፡ ከተካፈለ ፡ በኋላ ፡ ወደሌላ ፡ ሃይማኖት ፡ ቢመለስም ፡ ምንም ፡ ቢታዘዝለት ፡ ሊወርስ ፡ አይገባውም ።

፩ሺ፫፻፺፪ ሥርዋጽ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ካህነ ፡ ዝኩ ፡ ዘይ ወርስዎ ፡ ወወራስያኒሁ ፡ ይኩኑ ፡ ምእመናነ ፡ ወለእመ ፡ ኢተረክበ ፡ እምእዝማዲሁ ፡ ምእ መን ፡ ይኩን ፡ ንዋዩ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንተ ፡ ኮነ ፡ ካህነ ፡ ውስቴታ ። ወለእመ ፡ ኢኮነ ካህነ ፡ ወእልቦቱ ፡ ወራሲ ፡ ወእመ ፡ ውእቱ ፡ ምእመን ፡ ንዋዮ ፡ ያብእ ፡ ውስተ ፡ መዛግብተ ንጉሥ ። ወቀታሊሁኒ ፡ ለዘይወርስዎ ፡ እመሂ ፡ በገቢር ፡ እው ፡ መጠዎ ፡ ለዘይቀትሎ ፡ ወዘሂ ፡ ይትመከነይ ፡ ላዕለ ፡ ሕይወቱ ፡ እመሂ ፡ በሕ ምዝ ፡ እው ፡ በዘይመስሎ ፡ ለዝንቱ ።

፩ሺ፫፻፺፪ ሥርዋጽ ። ይህ ፡ የሚወርሱት ፡ ሰው ፡ ካህን ፡ ቢሆን ፡ ወራሾቹም ፡ እማኞች ፡ ይሁኑ ። ከዘ መዶቹ ፡ እማኝ ፡ ባይገኝ ፡ ገንዘቡ ፡ አገልጋይ ፡ ለነበረባት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይሁን ። ካህን ፡ ባይሆን ፡ ወራሽም ፡ ባይኖረው ፡ እርሱም ፡ እ ማኝ ፡ ቢሆን ፡ ገንዘቡን ፡ ከንጉሥ ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ያግቡ ። የሚወርሱትንም ፡ ሰው ፡ የገደለ ፡ በገቢ ርም ፡ (በማድረግም) ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ለሚ ገድል ፡ አሳልፎ ፡ ቢሰጠው ፡ በመርዝ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ በሚመስለው ፡ በሕይወቱ ፡ ላይ ፡ ምክ ንያት ፡ የሚፈልግ ፡ አይውረሰው ።

፩ሺ፫፻፺፫ ክፍል ፡ ዳግማዊ ፡ በእንተ ፡ ዘኢይወርሱ ፡ ዘእንበለ ፡ ትእዛዙ ፡ ለዘያወርስ ፡ እሉ ፡ እሙ ንቱ ፡ ውሉዱ ፡ ወእዝማዱ ፡ እለ ፡ ተወልዱ ፡ እምብእሲት ፡ ዘኢኮነት ፡ ሕጋዊተ ፡ በከመ ፡ እቅደምነ ፡ በእንተ ፡ እግብርት ፡ ወግዕዛን ፡ ወውሉድ ፡ መንዛህልላን ፡ እለ ፡ ይሜንንዎ ፡

፩ሺ፫፻፺፫ ሁለተኛ ፡ ክፍል ። ያለአውራሽ ፡ ትእዛዝ ፡ ስለማይወርሱት ፡ ይናገራል ። እሊህም ፡ የሕግ ፡ ሚስት ፡ ካልሆነች ፡ የተወለዱ ፡ ልጆቹና ፡ ዘመ ዶቹ ፡ ናቸው ። ስለባሮችና ፡ ስለነፃነት ፡ እንዳስ ቀደምን ። እርሱንም ፡ የሚንቁት ፡ ነዝኅላሎች ፡ ልጆች ፡ ያም ፡ ባይሆን ፡ የሚሰድቡት ፡ ወይም ፡

አንቀጽ ፡ ፵፱ ።

ሎቱ ፡ ወእመ ፡ አኮ ፡ ይብርሩዎ ፡ እው ፡ በወዳ
እቶሙ ፡ እምግብሩ ፡ ኀበ ፡ ግብር ፡ ሕሥምት ፡
ዘከመ ፡ ግብረ ፡ ተውኔት ፡ ወሥራይ ፡ ወእለ ፡
ይዜምዉ ፡ በብእሲቱ ፡ ለዘያወርስ ፡ እው ፡ በወ
ለቱ ፡ እው ፡ በእኅቱ ፡ እው ፡ በእሙ ፡ ወእለሂ ፡
ያስተዋድይዎ ፡ በዘያኀጕሉ ፡ ንዋዮ ፡ ኢይረሱ ፡
ዘእንበለ ፡ በጽሒፈ ፡ ትእዛዙ ፡ ለዘያወርስ ።
ወእንተሂ ፡ ተወሰበት ፡ እምቅድመ ፡ ፍጻሜ ፡
ኍልቍ ፡ ዘተወሰነ ፡ ላቲ ፡ በሕግ ፡ ወዘሂ ፡
ኀብአ ፡ ጽሒፈ ፡ ትእዛዝ ፡ በከመ ፡ ቀደመ ፡
ወተነግረ ፡ በእንቀጸ ፡ እውስቦ ፡ ወለእሉ ፡
ኵሎሙ ፡ ይደልዎ ፡ ለእውራሲ ፡ ከመ ፡ ይሰድ
ዶሙ ፡ እምርስቱ ፡ ዘይወርሱ ፡ በበመዓርጊ
ሆሙ ።

፩ሺ፫፻፶፮ ጠበ ፡ ፴ወ፫ቱ ፤ ወወልድ ፡ መንዛህልል ፡ ዘይ
ዘብጥ ፡ ወላድያኒሁ ፡ ወይፀርፎሙ ፡ ወትረ ፡ ወየ
ሐምዮሙ ፡ በጕሕሉት ፡ ወያሐምሞሙ ፡ በእበ
ሳሁ ፡ ወኢይትኤዘዝ ፡ ሎሙ ፡ እው ፡ ያመጽእ ፡
ላዕሌሆሙ ፡ ዓጸባ ፡ ዘይወበዶሙ ፡ ኀበ ፡ ሕዝብ፡
እለ ፡ ኢኮኑ ፡ ምእመናነ ፡ እው ፡ ያበተዋድዮሙ
ውዴተ ፡ ከመ ፡ ያብጽሖሙ ፡ ኀበ ፡ ዕዳ ፡ ዘዘዚ
እሁ ፡ እው ፡ ለእመ ፡ ረከቦሙ ፡ ለእበዊሁ ፡
ደዌ ፡ ዘዘልፍ ፤ እው ፡ ሶበ ፡ ረሰዑ ፡ ወደከሙ ፡
እመ ፡ ኢጸሐቀ ፡ ሎሙ ፡ ለተራድእቶሙ ፡ በእ
ምጣነ ፡ ከሂሎቱ ፤ እው ፡ ሶበ ፡ ኮነ ፡ በ፩ዱ ፡
እምኔሆሙ ፡ ተሞቅሖ ፡ እው ፡ ምንዳቤ ፡ ወኀ
ሠሠ ፡ ኀበ ፡ ወልዱ ፡ ከመ ፡ ይትሐበዮ ፡ ወኢተ
ወከፈ ፡ ቃሎ ፡ እንዘ ፡ ውእቱ ፡ ወልዱ ፡ ተባ
ዕት ፡ እው ፡ ከልእሙ ፡ ለወላድያኒሁ ፡ በትዕግ
ልት ፡ እምገቢረ ፡ ትእዛዝ ፡ እው ፡ ደመረ ፡
ነፍሶ ፡ ምስለ ፡ መንዛህልላን ፡ ዘእንበለ ፡ ምክረ
ወላድያኒሁ ፡ ወበኵሉ ፡ ዘይመስሎ ፡ ለዝንቱ ፡
ወቆመ ፡ በዘከመዝ ፡ ፍኖት ፡ ኢይስመይ ፡
እቡሁ ፡ ሎቱ ፡ ወኢይኩን ፡ ወልዶ ፡ ውእቱ ፡
በዝንቱ ፡ እርእያ ።

፩ሺ፫፻፶፯ ፶፯ ወበእምሳለ ፡ ዝንቱ ፡ ይኩን ፡ ሰደቶን ፡ ለወ
ለት ፡ ወለእኅት ፡ ወለእም ፡ ወካልእቲሆን ፡ ሶበ ፡
ተደመራ ፡ ምስለ ፡ ዘማውያን ፡ እው ፡ ሶበ ፡ ፈቀደ፡
፩ዱ ፡ እምወላድያን ፡ ከመ ፡ ያስተዋስብ ፡ ወለቶ ፡
እው ፡ ወለተ ፡ ወልዱ ፡ ወወሀባ ፡ ትልወተ ፡ በእ
ምጣነ ፡ ከሂሎቱ ፡ ወእበየት ፡ ወፈቀደት ፡ ግብረ
ዘያስተኀፍር ፡ እው ፡ ዐብደ ፡ ፩ዱ ፡ እምወላድ
ያን ፤ ወኢይጸሕቁ ፡ በቱ ፡ ውሉድ ። እው ፡ መን
ፈቀሙ ፡ እው ፡ ለእመ ፡ እልቦቱ ፡ ውሉድ ፡ ወጸ

ስለ ፡ ርስት ።

ከፈቃዱ ፡ ወደ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ በመውጣታቸው ፡
ይኸውም ፡ እንደ ፡ ዘፈንና ፡ እንደ ፡ ሥራይ ፡
ሥራ ፡ ያለ ፡ ነው ። በእውራሹ ፡ ሚስት ፡ ወይም
በልጁ ፡ ወይም ፡ በእኅቱ ፡ ወይም ፡ በእናቱ ፡
የሚሰስኑ ፤ ገንዘቡንም ፡ በሚያጠፉ ፡ ገንዘብ ፡
የሚከሱት ፡ ያለ ፡ እውራሽ ፡ የማዘዣ ፡ ደብ
ዳቤ ፡ አይውረሱ ። በሕግ ፡ ከተወሰነላት ፡ የቍ
ጥር ፡ ፍጻሜ ፡ አስቀድማ ፡ ያገባች ፡ ሴት ፡ የማ
ዘዣውንም ፡ ደብዳቤ ፡ የደበቀ ፡ አስቀድሞ ፡
በጋብቻ ፡ አንቀጽ ፡ እንደተነገረ ፡ እውራሽ ፡
እነዚዘን ፡ ሁሉ ፡ በየመዓርጋቸው ፡ ከሚወር
ሱት ፡ ከርስቱ ፡ ሊያባርራቸው ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ፫፻፶፮ ጠበ ፡ ፴፫ ። ወላጆቹን ፡ የሚማታ ፡ ዘወት
ርም ፡ የሚሰድባቸው ፡ በተንኮልም ፡ የሚያማ
ቸው ፡ በበደሉም ፡ የሚያሳዝናቸው ፡ የማይታዘ
ዝላቸው ፡ ወይም ፡ እማንያን ፡ ወደአልሆኑ ፡
ወገኖች ፡ የሚወስድ ፡ ጭንቅ ፡ የሚያመጣባ
ቸው ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ወደሆነ ፡ ዕዳ ፡ ሊያ
ደርሳቸው ፡ ነገር ፡ የሚሠራባቸው ፡ ነዘንላል ፡
ልጅ ፡ ወይም ፡ እባቶቹን ፡ የዘወትር ፡ ደዌ ፡
ቢያገኛቸው ፡ ወይም ፡ ባረጁና ፡ በደከሙ ፡ ጊዜ፡
እነርሱን ፡ ለመርዳት ፡ በተቻለው ፡ መጠን ፡ ባይ
ተጋ ፡ ወይም ፡ ከእነርሱ ፡ በአንዱ ፡ እሥራት ፡
ወይም ፡ መከራ ፡ ቢሆንበትና ፡ ልጁ ፡ እንዲዋ
ሰው ፡ ቢፈልግ ፡ ወንድ ፡ ልጁ ፡ ሲሆን ፡ ቃሉን ፡
ባይቀበለው ፡ ወይም ፡ ወላጆቹን ፡ በኃይል ፡ ትእ
ዛዝ ፡ ከማድረግ ፡ ቢከለክላቸው ፡ ወይም ፡ ያለወ
ላጆቹ ፡ ፈቃድ ፡ ራሱን ፡ ከነዘንላሎች ፡ ጋራ ፡
፩ ፡ ቢያደርግ ፡ ይህን ፡ በመሰለው ፡ ሁሉ ፡ በእን
ደዚህ ፡ ያለ ፡ መንገድ ፡ ቢጸና ፡ ለእርሱ ፡ እባቱ ፡
እይባል ። እርሱም ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ልጁ
እይሁን ።

፩ሺ፫፻፶፯ ፶፯ ለሴት ፡ ልጅ ፡ ለእኅትም ፡ ለእናትም ፡ ለሌሎ
ቻቸውም ፡ ከዘማውያን ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ቢሆኑ ፡
በዚህ ፡ እምሳል ፡ መባረራቸው ፡ ይሁን ። ወይም
ከወላጆች ፡ አንዱ ፡ ሴት ፡ ልጁን ፡ ወይም ፡ የወ
ንድ ፡ ልጁ ፡ ሴት ፡ ልጅን ፡ ሊድር ፡ ቢወድና ፡
የተቻለውን ፡ ያህል ፡ ትልወት ፡ ቢሰጣት ፡
እንቢ ፡ ብትልም ፡ የሚያሳፍር ፡ ሥራም ፡ ብት
ወድ ፡ ወይም ፡ ከወላጆች ፡ አንዱ ፡ እእምሮውን
ቢያጣ ፡ ልጆቹም ፡ በሙሉ ፡ ወይም ፡ እኩሌ

ውዐ ፡ በእንተ ፡ ጸሕቅ ፡ ዘኢኮኑ ፡ እምእዝማዲሁ ፡
እለ ፡ ይወርስዎ ፡ ዘእንበለ ፡ ትእዛዝ ፡ ወኢጽሒፉ ፡
ቦቱ ፡ ወእምዝ ፡ ሡነየ ፡ ተፈልጦቱ ፡ እምደዌሁ ፡
ቦቱ ፡ ሥልጣን ፡ እምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ሶበ ፡ ፈቀደ ፡
ከመ ፡ ይጽሐፍ ፡ ትእዛዝ ፡ በዘይሬስዮሙ ፡ ለው
ሉድ ፡ አው ፡ ለአዝማዲሁ ፡ እለ ፡ ተኀየደዎ ፡
በጊዜ ፡ ምንዳቤሁ ፡ ሰዱዳነ ፡ እምነ ፡ ርስቱ ፡
ፍዳ ፡ ዘከሕዱ ፡ ጸጋሁ ።

፩ሺ.፫፻.፺፱ ወለእመ ፡ ርእዮ ፡ ፩ዱ ፡ ነኪር ፡ በደዌሁ ፡
ወአዝማዲሁ ፡ እንዘ ፡ ይትኄየደዎ ፡ ወተራኅ
ርኀ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወፈቀደ ፡ ከመ ፡ የሐሊ ፡ ቦቱ ፡
ይንግሮሙ ፡ ከመ ፡ ይስተብዎ ፡ ወያስተሐምሙ
ሎቱ ፡ ወእመ ፡ ኢተሠጥውዎ ፡ ወነሥኦ ፡ ውእቱ ፡
ነኪር ፡ ኀበ ፡ ማኅደሩ ፡ ወተዐውቀ ፡ ከመ ፡
ውእቱ ፡ አስተዋፅአ ፡ ሲሳዮ ፡ እምንዋዩ ፡ እስከ ፡
ሰለተ ፡ ሞቱ ፡ ይደልዎ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይባእ ፡
ውስተ ፡ ርስቱ ፡ ከመ ፡ ፩ዱ ፡ እምድልዋን ፡ ለወ
ሪሶቱ ።

፩ሺ.፬፻ ዓዲ ፡ ለእመ ፡ ረከቦ ፡ ለ፩ዱ ፡ እምወላድያን ፡
ስደት ፡ ወተሞቅሐ ፡ ወኢየፍጠኑ ፡ ውሉዱ ፡
ኵሎሙ ፡ አው ፡ መንፈቆሙ ፡ በእንተ
አድኅኖቱ ፡ በእምጣነ ፡ ከሂሎቶሙ ፡ ይደል
ዎኬ ፡ ሎቱ ፡ እምድኅረ ፡ ድኅነ ፡ ከመ ፡ ያስተጸ
ንሶ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ከሐደ ፡ በጽሒፈ ፡ ትእዛዙ ፡
ወኢይደልዎ ፡ ከመ ፡ ያውርሶሙ ፡ ወለእመ ፡
ኢያድኅንዎ ፡ እምነ ፡ ሙቃሔ ፡ በተኀይዮ
ቶሙ ፡ ወሶበ ፡ሞተ ፡ በሙቃሔ ፡ ኢይረስዩ ፡
እንከ ፡ በእንተ ፡ ተኀይዮቶሙ ። ወይኩን ፡
ርስቱ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወይትወሀብ ፡
ለመድኃኒተ ፡ ሙቁሓን ፡ እስከ ፡ ይኩኑ ፡ በዘ
ይድኀኑ ፡ ቦቱ ፡ እልክቱ ፡ ይትወሀብ ፡ በጸሕቅ ፡
ለመድኃኒተ ፡ ካልኣን ።

፩ሺ.፬፻፩ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ሙቁሕ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ውሉድ ፡
ወኮነ ፡ ሀኬት ፡ እምካልኣኒሆሙ ፡ ለእለ ፡ ይበ
ውኡ ፡ ውስተ ፡ ርስቱ ፡ እንበለ ፡ ትእዛዝ ፡ ወተ
ሃከዩ ፡ ለአድኅኖቱ ፡ እስከ ፡ ይመውት ፡ በሙ
ቃሔሁ ፡ ኢየሀቡ ፡ ርስቶ ፡ ለ፩ዱሂ ፡ እምእለ ፡
ተሀከዩ ፡ ግብረ ፤ ወእመሂ ፡ ኮነ ፡ ዘጸሐፈ ፡
ሎሙ ፡ እምቅድመ ፡ ሙቃሔሁ ።

፩ሺ.፬፻፪ ወይጸናዕ ፡ ካዕበ ፡ ዝንቱ ፡ ነገር ፡ ውስተ ፡
ነኪር ፡ ዘአቀመ ፡ ሎቱ ፡ ሙቁሕ ፡ እምቅድመ ፡
ተሞቅሖቱ ፡ ይኩን ፡ ወራሴ ። ወናሁ ፡ እእመረ ፡



ቶቹ ፡ ባያስቡለት ፡ ወይም ፡ ልጆች ፡ ባይኖሩት ፡
ያለትእዛዝ ፡ ከሚወርሱት ፡ ከዘመዶቹ ፡ ያልሆ
ኑትን ፡ ስለችግሩ ፡ ቢጠራ ፡ ባይተጉለት ፡ ከዚህ ፡
በኋላ ፡ ከደዌው ፡ መለየቱ ፡ ቢያምር ፡ (ቢድን) ፡
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በመከራው ፡ ጊዜ ፡ ቸል ፡ ያሉ
ትን ፡ ልጆቹን ፡ ወይም ፡ ዘመዶቹን ፡ ከርስት ፡
የተነቀሉ ፡ በሚያደርጋቸው ፡ ገንዘብ ፡ ትእዛዝ
ሊጽፍ ፡ ቢወድ ፡ ሥልጣን ፡ አለው ። ስጦታ
ዉን ፡ ስለካዱ ።

፩ሺ.፫፻.፺፱ በሕማሙ ፡ ጊዜ ፡ ዘመዶቹ ፡ ቸል ፡ ሲሉት ፡
አንድ ፡ ባዕድ ፡ ሰው ፡ አይቶ ፡ ሊራራለትና ፡
ሊያስብለት ፡ ቢወድ ፡ እንዲጠብቁትና ፡ እንዲ
ተጉለት ፡ ይንገራቸው ። ባይቀበሉት ፡ ግን ፡ ያ ፡
ባዕድ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ቢወስደውና ፡ እስከ
ሚሞትበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ለምግቡ ፡ ከገንዘቡ ፡
እንዳወጣጣለት ፡ ቢታወቅ ፡ ሊወርሱት ፡ ከሚ
ገባቸው ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ከርስቱ ፡
መግባት ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ.፬፻ ዳግመኛም ፡ ከወላጆቹ ፡ አንዱን ፡ ሰደትና ፡ እሥ
ራት ፡ ቢያገኘው ፡ ልጆቹ ፡ ሁሉ ፡ ወይም ፡ እኩ
ሌቶቹ ፡ በተቻላቸው ፡ መጠን ፡ እርሱን ፡ ለማ
ዳን ፡ ባይፋጠኑ ፡ ከዳነ ፡ በኋላ ፡ ትእዛዙን ፡ በመ
ጻፍ ፡ እነርሱን ፡ መካዱን ፡ ሊያጸና ፡ ይገባዋል ።
ሊያወርሳቸውም ፡ አይገባውም ። ቸል ፡ በማለ
ታቸው ፡ ከእሥራቱ ፡ ባያድኑት ፡ ስለቸልተኞነ
ታቸው ፡ በእሥራት ፡ ቢሞት ፡ አይውረሱት ፡፡
ርስቱም ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይሁን ። እነር
ሱም ፡ በእርሱ ፡ የሚድኑበት ፡ እስኪሆኑ ፡
ድረስ ፡ ለእሥረኞች ፡ መድኃኒት ፡ ሁኖ ፡
(መፈቻ) ፡ ይሰጥ ። ለሌሎችም ፡ መድኃኒትነት ፡
በትጋት ፡ ይሰጥ ።

፩ሺ.፬፻፩ እሥረኛው ፡ ልጆች ፡ የሌሉት ፡ ቢሆን ፡ ያለ ፡
ትእዛዝ ፡ ወደ ፡ ርስቱ ፡ ከሚገቡት ፡ ከሌሎቹ ፡
ስንፍና ፡ ቢሆን ፡ በእሥራቱ ፡ እስኪሞት ፡
ድረስ ፡ እርሱን ፡ ለማዳን ፡ ቸል ፡ ቢሉ ፡ ከመታ
ሠሩ ፡ በፊት ፡ የጻፈላቸውም ፡ ቢሆን ፡ ሥራዉ
ን ፡ ቸል ፡ ካሉት ፡ ወገን ፡ ለአንዱስ ፡ እንኳ ፡
ርስቱን ፡ አይስጡ ።

፩ሺ.፬፻፪ ዳግመኛም ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ወራሽ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ
ከመታሠሩ ፡ አስቀድሞ ፡ እሥረኛው ፡ ያወሰነ
ለት ፡ በባዕድ ፡ ሰው ፡ ላይም ፡ ይጽና ። መታ

አንቀጽ ፡ ፴፱ ።

ዘንተ ፡ ወተበወረ ፡ ጽሒቀ ፡ ለአድኅኖቱ ፡ እምነ፡
ሙቃሒሁ ፡ ይከውን ፡ ዝንቱ ፡ ዘንኡ ፡ ድልው
ቦቱ ፡ እመ ፡ ኮነ ፡ ዘኀለፈ ፡ ዓመታቲሁ ፡ እም፲
ወ፰ቱ ፡ ዓመት ።

፩ሺ.፬፻፫ ወኵሉ ፡ ዘተውይጠ ፡ እምንዋዩ ፡ ለቤዛ ፡ ዚአሁ
እመኒ ፡ በእንግዘ ፡ አው ፡ በልቃሕ ፡ ለዝንቱ ፡
ሠናይ ፡ ወጽኑዕ ፡ ንቢሮቱ ፡ ወይደልዎ ፡ ለዘይትገ
ብእ ፡ እምነ ፡ ሙቃሔ ፡ ከመ ፡ ይፍዲ ፡ ወይደ
ልዎ ፡ አግብአታ ፡ እስመ ፡ ኮነ ፡ በእንተ ፡ መድ
ኃኒቱ ፡ ወበቀኑዔቱ ፡ ዚአሁ ።

፩ሺ.፬፻፬ ወሶበሂ ፡ ወሀበ ፡ ወራሲ ፡ ለአውራሲሁ ፡ ፈውሰ፡
ዘያማስን ፡ ልበ ፡ አው ፡ ሰአሎ ፡ ከመ ፡ ይርድእ፡
ወራሲ ፡ ለዘያወርሶ ፡ እንዘ ፡ ይትከሀሎ ፡ ተራድ
አቱ ፡ ወኢረድአ ፡ እስከ ፡ ይመውት ፡ አው ፡
ተአሰረ ፡ ኢያረስ ፡ ወኢያንግእ እምዘ ፡ አዘዘ ፡
ቦቱ ፡ ሎቱ ፡ እምድኅረ ፡ ዝንቱ ። ወእመሰ ፡
ኮነ ፡ ወራሲ ፡ ዘኢይትከሀሎ ፡ ከመ ፡ ይርድእ ፡
በእንተ ፡ ከዊኖቱ ፡ በሃመ ፡ ወጽሙመ ፡ አው ፡
ድውየ ፡ አው ፡ ሀብደ ፡ ኢያክልእዎ ፡ ርስቶ ።

፩ሺ.፬፻፭ ወኵሉ ፡ ዘተዘክረ ፡ እምዘ ፡ ይደልዎሙ ፡ ለው
ሉድ ፡ በእንተ ፡ አበዊሆሙ ፡ ይደልዎሙ ፡ ለአ
በው ፡ በእንተ ፡ ውሉዶሙ ፡ በአምሳሊሆሙ ፡
ወፍትሕ ፡ ዘልው ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ወራሲ ፡ ወለዘ
ይወርሶ ፡ ኪያሁ ፡ ምስለ ፡ ኵሎሙ ፡ ወራስያን ፡
እመ ፡ ኢጸንዐ ፡ ምክንያተ ፡ ክልእ ፡ ዘወረሰ ፡
ወውእቱ ፡ እምድኅረ ፡ ኮነ ፡ ግብረ ፡ ትእዛዝ ፡
እመሂ ፡ ለዘመድ ፡ አው ፡ ለነኪር ።

፩ሺ.፬፻፮ ወዘንደገ ፡ ሎቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘይደልዎ ፡ በው
ስተ ፡ ሕግ ፡ ወዘኢይደልዎ ፡ ለተዋርሶ ፡ ወካ
ልእ ፡ ዘተዘክረ ፡ ለዘማውያን ፡ ወተነግረ ፡
ዝንቱ ፡ በአብጥሊሳት ፡ ወእለሂ ፡ ይመስልዎሙ፡
ድሙራን ፡ በላዕሌሆሙ ።

፩ሺ.፬፻፯ ወመትልወ ፡ ዝንቱ ፡ ዘኮነ ፡ በእስተማስሎ ፡
ወኢይትአመር ፡ ግብሩ ። ወዝንቱኒ ፡ ይትከ
ፈል ፡ ኀበ ፡ ፪ቱ ፡ አክፋል ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡
ለእመ ፡ ሞቱ ፡ ፪ቱ ፡ እምወራስያን ፡ አው ፡ ፫ቱ
በውስተ ፡ ንጊድ ፡ አው ፡ በታሕተ ፡ ቤት ፡ ዘወ
ድቀ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ አው ፡ በተሰጥሞ ፡ ባሕር ፡
አው ፡ በዋዕየ ፡ እሳት ፡ አው ፡ ለእመ ፡ ሞቱ ፡
መንፈቆሙ ፡ በዘከመዝ ፡ ወመንፈቆሙኒ ፡ በዘ
ኢኮነ ፡ ከማሁ ። ወፈድፋደሰ ፡ ለእመ ፡ ኢተዐ
ውቀ ፡ መኑ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘሞተ ፡ ወመኑ ፡ ዘተ
ርፈ ፡ እምድኅረ ፡ ካልኡ ፡ ኢያረስዎ ፡ ለ፩ዱ ፡

ስለ ፡ ርስት ።

ሠሩን ፡ ዐውቆ ፡ ከእሥራቱ ፡ ለማዳን ፡ መትጋ
ትን ፡ ቸል ፡ ቢል ፡ ዕድሜው ፡ ከአሥራ ፡ ስም
ንት ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ከሆነ ፡ ይህ ፡ ፍርድ ፡ በእ
ርሱም ፡ ላይ ፡ የተገባ ፡ ይሆናል ።

፩ሺ.፬፻፫ ለእርሱ ፡ ቤዛ ፡ ከገንዘቡ ፡ የተሸጠው ፡ ሁሉ ፡
በመያዣ ፡ ወይም ፡ በብድር ፡ ቢሆን ፡ ይህ ፡ መደ
ረጉ ፡ መልካም ፡ የጸናም ፡ ነው ። ከእሥራት ፡ የተመ
ለሰውም ፡ ሰው ፡ ሊከፍል ፡ ይገባዋል ። እርሷንም
መመለስ ፡ ይገባዋል ። እርሱን ፡ ለማዳንና ፡
ስለእርሱ ፡ ጥቅም ፡ ተደርጓልና ።

፩ሺ.፬፻፬ ወራሽ ፡ ለአውራሹ ፡ ልብ ፡ የሚያጠፋ ፡ መድ
ኃኒት ፡ ቢሰጠው ፡ ወይም ፡ ወራሽ ፡ እውራ
ሹን ፡ እንዲረዳው ፡ ቢለምነውና ፡ ሊረዳው ፡ ሲ
ቻለው ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ ባይረዳው ፡
ወይም ፡ ቢታሠር ፡ አይውረስ ። ከዚህም ፡ በኋላ
ያዘዘለትን ፡ ገንዘብ ፡ አይውሰድ ። ወራሽ ፡ ዲዳ ፡
ደንቆሮ ፡ ወይም ፡ በሽተኛ ፡ ወይም ፡ ዕብድ ፡
በመሆኑ ፡ ምክንያት ፡ ሊረዳው ፡ የማይችል ፡
ቢሆን ፡ ግን ፡ ርስቱን ፡ አይከልክሉት ።

፩ሺ.፬፻፭ ልጆች ፡ ለአባቶቻቸው ፡ ሊያደርጉት ፡ ከሚገባ
ቸው ፡ የተነገረው ፡ ሁሉ ፡ አባቶችም ፡ ስለ ፡
ልጆቻቸው ፡ በምሳሌያቸው ፡ ይገባቸዋል ።
በወራሽ ፡ ሁሉ ፡ ላይና ፡ ከወራሾችም ፡ ሁሉ ፡
ጋር ፡ እርሱን ፡ ስለሚወርሰው ፡ ፍርድ ፡ አለ ።
ከውርስ ፡ የመከልከል ፡ ምክንያት ፡ ካልጸና ።
ይኸውም ፡ ለዘመድ ፡ ወይም ፡ ለባዕድ ፡ ቢሆን ፡
የትእዛዝ ፡ ሥራ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ ነው ።

፩ሺ.፬፻፮ በሕግ ፡ ለመውረስ ፡ ከሚገባውና ፡ ከማይገባው
በቀር ፡ የተወለትም ፡ ለዘማውያን ፡ የተነገረው፡
ሌላውም ፡ ይህ ፡ በአብጥሊሳት ፡ ተነግሯል ።
የሚመስሏቸውም ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ተጨም
ረዋል ።

፩ሺ.፬፻፯ ይህንም ፡ የሚከተለው ፡ ሥራው ፡ የማይታ
ወቅ ፡ በማስመስል ፡ የሆነ ፡ ነው ። ግብሩም
አይታወቅም ፡ ይህም ፡ ከሁለት ፡ ክፍል ፡ ይከ
ፈላል ። ከነዚህም ፡ አንዱ ፡ ከወራሾች ፡ ሁለቱ ፡
ወይም ፡ ሦስቱ ፡ እሩቅ ፡ መንገድ ፡ በመሄድ ፡
ወይም ፡ በላያቸው ፡ ቤት ፡ ፈርሶ ፡ ተጭኗ
ቸው ፡ ወይም ፡ በባሕር ፡ ውስጥ ፡ በመስጠም ፡
በእሳት ፡ ቃጠሎ ፡ ቢሞቱ ፡ ወይም ፡ እኩሌቶቹ፡
በእንደዚህ ፡ ባለ ፡ አደጋ ፡ እኩሌቶቹም ፡ እንደ
ዚህ ፡ ባልሆነ ፡ አደጋ ፡ ቢሞቱ ፡ ይልቁንም ፡
ከእነርሱ ፡ የሞተው ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ ከሌላ

አንቀጽ ፡ ፵፪ ።

ወለካልኡ ፡ ኢይረስዎሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ዘእን
በለ ፡ እለ ፡ ይደልዎሙ ፡ ይረሱ ፡ ኪያሁ ፡ እም
ሕያዋን ፡ ወእኮ ፡ እምዉታን ፡ እለ ፡ ኢተዐ
ውቀ ፡ ዘላዌሆሙ ፡ በቀዲም ፡ ወበተድኅሮ ።

፩ሺ፬፻፰ ወካልእ ፡ ክፍል ፡ ዘይከልእ ፡ እምተሀብሎ ፡
ለሰብ ፡ ንዋዮሙ ፡ ለእለ ፡ ኢተጠየቀ ፡ ሀልዎ
ቶሙ ፡ እንዘ ፡ ይትወላወሉ ፡ በእንተ፡እሆሙ ፡
ዘከመ ፡ ሙቱሕ ፡ ወዘንጉደ ። ወፈድፋደሰ ፡ ለዘ
ተነጥአ ፡ ዘዚኦሁ ፡ ኢይክፍል ፡ ንዋዮ ፡ ዘሀለወ ፡
እንበለ ፡ ያቅም ፡ ጥያቄ ፡ በእንተ ፡ ሞቱ ፡ አው ፡
ለእመ ፡ ኀለፈ ፡ ኑኅ ፡ ዕድሜሁ ፡ ዘንማይቱ ፡
ወፈታሒ ፡ ይፍታሕ ፡ ከመ ፡ ዘነበረ ፡ መጠነ ፡
ዝንቱ ፡ ዕድሜ ፡ ኢየሐዩ ።

፩ሺ፬፻፱ ወለእመቦ ፡ ዘሞተ ፡ እምእዝማዲሁ ፡ እለ ፡
ሀለዉ ፡ ተገብረ ፡ ውስተ ፡ መክፈልት ፡ በው
ይት ፡ እስመ ፡ መጠነ ፡ ሕይወቱከ ፡ ምስለ ፡
ታሕጸጸ ፡ ንዋዩ ፡ እምእለ ፡ ሀልዋን ፡ በሕይ
ወቱ ፡ በከመ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ሎቱ ፡ ወልድ ፡
ሀልወ ፡ ወሞተ ፡ ወልደ ፡ እኁሁ ፡ ለንጉዲ ፡ ወኢ
ኮነ ፡ ለንጉዲ ፡ ዘየሀውዶ ። እስመኬ ፡ በመጠነ ፡
ሕይወቱ ፡ ይትከላእ ፡ ርስት ፡ እምወልዱ ፡ ወይ
ደሉ ፡ ከመ ፡ ያማኅፅን ፡ መክፈልቶ ፡ እስከ ፡
ይትአመር ፡ ዜናሁ ፡ ወይትፈታሕ ፡ ውስቴቱ ፡
በአእምሮ ፡ አው ፡ ዘይመስሎ ።

ስለ ፡ ዳኛ ።

ውም ፡ በኋላ ፡ የቀረ ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ ሳይታ
ወቅ ፡ እንዲንና ፡ ሁለተኛውን ፡ አይውረሱት ።
በመቅደምና ፡ በመከተል ፡ መኖራቸው ፡ ካልታ
ወቀ ፡ ከሙታን ፡ ወገን ፡ ያይደለ ፡ ከሕያዋን ፡
ወገን ፡ እርሱን ፡ ሊወርሱት ፡ ከሚገባቸው ፡
በቀር ፡ ሁሉንም ፡ አይውረስአቸው ።

፩ሺ፬፻፰ ፪ኛ ፡ ክፍል ። መኖራቸው ፡ ያልተረጋገጠላቸ
ውን ፡ ሰዎች ፡ ገንዘብ ፡ ስለእነርሱ ፡ እየተጠራ
ጠሩ ፡ ከመደፋፈር ፡ የሚከለክል ፡ ነው ። ይኸ
ውም ፡ እንደእሥረኛ ፡ እሩቅ ፡ አገር ፡ እንደሄደ ፡
ሰውም ፡ ያለ ፡ ነው ። ይልቁንም ፡ ወሬው ፡ የታ
ጣውን ፡ ሰው ፡ ስለሞቱ ፡ እርግጡን ፡ ሳያስረዳ ፡
በአገር ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ገንዘቡን ፡ አይክፈል ።
ወይም ፡ እሩቅ ፡ አገር ፡ የሄደ ፡ ሰው ፡ የመሄዱ ፡
ዘመን ፡ ልክ ፡ ቢያልፍ ፡ ዳኛ ፡ በዚህ ፡ በኖረበት፡
ዘመን ፡ ልክ ፡ እንደማይኖር ፡ ገምቶ ፡ ይፍረድ ።

፩ሺ፬፻፱ በዙረት ፡ ሳለ ፡ ካሉ ፡ ዘመዶቹ ፡ ወገን ፡ የሞተ ፡
ቢኖር ፡ እነዋሩ ፡ ካሉት ፡ ወገን ፡ ነውና ፡ ከዋ
ቂት ፡ ገንዘቡ ፡ ጋራ ፡ ፈንታውን ፡ ከፍለው ፡ ሊ
ያኖሩለት ፡ ተገባ ። በሃገር ፡ የሚኖር ፡ ልጅ ፡
ቢኖረው ፡ እሩቅ ፡ አገር ፡ የሄደው ፡ ሰው ፡ የወን
ድሙ ፡ ልጅ ፡ ቢሞት ፡ እሩቅ ፡ አገር ፡ የሄደው
ንም ፡ የማያገለግለው ፡ ቢሆን ፡ በሕይወት ፡ ባለ
በት ፡ ልክ ፡ ርስት ፡ ከልጁ ፡ ይከለከላልና ። ወሬ
ው ፡ እስኪታወቅ ፡ በእውቀት ፡ ወይም ፡ በሚመ
ስለው ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ እስኪፈረድ ፡ ድረስ ፡
ድርሻውን ፡ አደራ ፡ ሊያስጠብቅ ፡ ይገባል ።

---

## አንቀጽ ፡ ፵ወ፫ቱ

በእንተ፡ ፈታሒ፡ ወዘይደልዎ፡ ወበእንተ፡
ስማዕታት ።

፩ሺ፬፻፲ወውእቱ፡ ፲ወ፫ቱ፡ ምዕራፍ። እምዘተጽሕፈ፡
በውተ፡ ሕገጋት፡ እምሳለ፡ ሥርው፡ ወዓጽቅ፡
ወተጋብአ፡ ትሩፋቲሁ፡ በከመ፡ እግህደ፡ ቦቱ፡
በፍጻሜ፡ አእምሮ።

፩ሺ፬፻፲፩ምዕራፍ፡ ቀዳማዊ፡ በእንተ፡ ሢመተ፡
ፍታሒ። ወፈታሒስ፡ ውእቱ፡ ሊቀ፡ ካህናት፡
ወውእቱ፡ ሊቀ ጳጳሳት፡ አው፡ ኤጲስቆጶስ፡
አው፡ ዘአትለውዎ፡ እሙንቱ፡ ወረስዮዎ፡ ሀየ
ንቴሆሙ፡ በእንተ፡ ፍትሕ፡ ዘሎ፡ ለለ፩፡ ፩ዱ፡
እምኔሆሙ፡ በውስተ፡ መንበሩ፡ እምካህናት፡
እለ፡ ድልዋን፡ ለዝንቱ።

## አንቀጽ፡ ፵፫።

ስለዳኛና፡ ስለሚገባው፡ ስለምስክሮችም ፡
ይናገራል ።

፩ሺ፬፻፲እርሱም፡ አሥራ ሦስት፡ ምዕራፍ፡ ነው። በሥ
ርና፡ በጫፍ፡ አምሳል፡ በትሩፋት፡ መሰብሰብ፡
በሕገጋት፡ ከተጻፈው፡ የተገኘ፡ ነው። በእው
ቀት፡ መጨረሻ፡ እንደተገለጠው።

፩ሺ፬፻፲፩መጀመሪያ፡ ምዕራፍ፡ ስለዳኛው፡ ሹመት፡
ይናገራል። ዳኛውም፡ የካህናት፡ አለቃ፡ ነው።
እርሱም፡ ሊቀ፡ ጳጳሱ፡ ወይም፡ ኤጲስቆጶሱ፡
ወይም፡ እነርሱ፡ ያስከተሉት፡ (የሾሙት)፡
ከካህናት፡ በወንበሩ፡ ስለፍርድ፡ በእነርሱ፡
ፈንታ፡ያደረጉት፡ ነው።

፩ሺ፬፻፲፪ ወሢመተ ፡ ፈታሒስ ፡ ድልው ፡ ውእቱ ፡ በፍጻሜ ፡ ሕግ ፡ ወፍጥረት ። ወዘይቀድምስ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ እግዚእብሔር ፡ ልዑል ፡ በኦሪት፡ ውስተ ፡ መጽሐፍ ፡ ኃምስ ፡ ሢሙ ፡ ለክሙ ፡ ፈታሕተ ፡ በኵሉ ፡ አህጉሪክሙ ፡ እንተ ፡ ይሁበክሙ ፡ እግዚእብሔር ፡ አምላክክሙ ፡ ከመ ፡ ይፍትሑ ፡ ማእከለ ፡ ሰብእ ፡ ፍትሐ ፡ ርቱዐ ፡ ዘኢያጸንኑ ፡ በጊዜ ፡ ፍትሕ ፡ ወኢይነሥኡ ፡ ገጸ ወኢሕልያነ ፡ እስመ ፡ ሕልያን ፡ ያዐውር ፡ አዕይንተ ፡ ጠቢባን ፡ ከመ ፡ ኢይርአዩ ፡ ጽድቀ ፡ ወይዌልጥ ፡ ቃለ ፡ ርቱዐ ።

፩ሺ፬፻፲፫ ወዳግማዊኒ፡እስመ ፡ ተጋብእ ፡ ሀገራዊ ፡ ኢይትኀደግ ፡ ዘእንበለ ፡ ትኩን ፡ ተጋእዞ ፡ ቦቱ ፡ እምነ ፡ ግብራት ፡ ወኢይትፌጸምኬ ፡ በሠናይ ፡ ዘእንበለ ፡ ፈታሒ ፡ ዘይፈትሕ ፡ ማእከለ ፡ ተጋእዝያን ፡ ለጽኑዕ ፡ ወለድኩም ፡ ለለባዊ ፡ ወለዐብድ ፡ በከመ ፡ ይደሉ ፡ ለገቢረ ፡ ርትዕ ።

፩ሺ፬፻፲፬ ወዘሂ ፡ ጸነ ፡ እምትእዛዘ ፡ ፈታሒ ፡ ይኤምር ፡ ካዕበ ፡ ከመ ፡ ይደሉ ፡ አቅሞቱ ፡ ወሥርዓተ ፡ አቅሞቱኒ ፡ ናሁ ፡ ይነብር ፡ እምትእዛዘ ፡ ፍትሕ ። ወይመርሕ ፡ ካዕበ ፡ ኀበ ፡ ይሊወ ፡ ሢመት ፡ እስመ ፡ ትእዛዘ ፡ ሢመትኒ ፡ ናሁ ፡ ቀደመ ፡ ተነግሮ ፡ በቀኖናት ፡ እምትእዛዘ ፡ ሢመት ፡ ዘክህናት ፡ ወሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ወይደሉ ፡ ከመ ፡ ነእዝዝ ፡ በዝየኒ ፡ ትእዛዘ ፡ ሢመተ ፡ ፍትሕ ፡ እምኀበ ፡ ውእቱ ፡ ፈታሒ ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ይክውን ፡ ሢመቱ ፡ ሠናየ ፡ ወትቀውም ፡ ፍትሐ ፡ ዚአሁ ። ወኍላቌሆን ፡ ፲ወ፫ቱ ፡ ትእዛዛት ።

፩ሺ፬፻፲፭ ቀዳሚሆን ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ብእሲ ፡ ወዝንቱ ፡ ዘያስተጋብእ ፡ አብጽሖተ ፡ መጠን ፡ ዘብእሲ ፡ ወብጽሖትሰ ፡ ብጹሐ ፡ አምጣን ፡ ዘፈጸመ ፡ ሕገ ፡ ውርዛዌ ። ወዘእንበሌሁሰ ፡ ኢይትፌጸም ፡ ልቡና ፡ ወኢይበቍዕ ፡ ለሢመት ፡ ከመ ፡ ይፍታሕ ፡ ማእከለ ፡ ዐቢያን ፡ ወልኂቃን ፡ ወዘ ይመስሎሙ ፡ ወኢይሤኒ ፡ ከመ ፡ የሀልዉ ፡ ዘእምሳለ ፡ እሉ ፡ ቅድሜሁ ፡ ለዘኢበጽሐ ፡ ኀበ፡ መጠን ፡ ከመ ፡ ይፍታሕ ፡ ሎሙ ። ወበላዕሌሆሙ ፡ ሎሙ ፡ ብሂል ፡ ለእለ ፡ ይመውዑ ፡ ወበ ላዕሌሆሙ፡ሎሙ ፡ ብሂል፡ለእለ ፡ ይትመውዑ ።

፩ሺ፬፻፲፮ ወበእንተ ፡ ተባዕትኒ ፡ እስመ ፡ ብእሲ ፡ ርእሳ ፡



፩ሺ፬፻፲፪ የዳኛ ፡ መሾምስ ፡ በሕግና ፡ በፍጥረት ፡ ፍጻሜ የተገባ ፡ ነው ። የሚቀድመው ፡ ግን ፡ ልዑል ፡ እግዚእብሔር ፡ በኦሪት ፡ በአምስተኛው ፡ መጽሐፍ ፡ ፈጣሪያችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚሰጣችሁ ፡ አገሮቻችሁ ፡ ሁሉ ፡ በሰዎች ፡ መካከል ፡ የቀና ፡ ፍርድ ፡ ይፈርዱ ፡ ዘንድ ፡ ለራሳችሁ ፡ ዳኞችን ፡ ሹሙ ። በፍርድ ፡ ጊዜ ፡ የማያደሉ ፡ ፊት ፡ አይተው ፡ መማለጃ ፡ (ጉቦ) ፡ የማይቀበሉ ፡ መማለጃ ፡ (ጉቦ) ፡ እውነትን ፡ እንዳያዩ ፡ የብልሆችን ፡ ዓይን ፡ ያሳውራልና ። የቀናውንም ፡ ፍርድ ፡ ይለውጣልና ፡ ብሎ ፡ እንደተናገረ ። (ዘዳግ ፡ ፲፮ ፡ ፲፰ - ፳) ።

፩ሺ፬፻፲፫ ሁለተኛውም ፡ በሀገር ፡ የምትደረግ ፡ ስብሰባ ፡ ክሥራ ፡ ወገን ፡ ክርክር ፡ ሳይሆንባት ፡ አትፈታምና ። በተጣሉት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ለብርቱና ለደካማ ፡ ለዐዋቂና ፡ ላለዐዋቂም ፡ ቅን ፡ ለመሥራት ፡ እንደሚገባ ፡ የሚፈርድ ፡ ዳኛ ፡ ከሌለ፡ በመልካም ፡ አይፈጸምምና ።

፩ሺ፬፻፲፬ ክዳኛ ፡ ትእዛዝ ፡ የጸነነውንም ፡ (የተሰወረውንም) ፡ ሁለተኛ ፡ መቅጠር ፡ እንደሚገባ ፡ ያመለክታል ። የቀጠሮው ፡ ሥርዓትም ፡ ከፍርድ ፡ ትእዛዝ ፡ የተነሣ ፡ እነሆ ፡ ይወሰናል ። ዳግመኛም ፡ ለሹመት ፡ ወደመገባት ፡ ይመራል ። እነሆ ፡ የሹመት ፡ ትእዛዝ ፡ ክካህናትና ፡ ከሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ሹመት ፡ ትእዛዝ ፡ የተነሣ ፡ አስቀድሞ ፡ በመጻሕፍት ፡ ተነግሯልና ፡ በዚህም ፡ ሹመቱ ፡ መልካም ፡ የምትሆንበትንና ፡ ፍርዱ ፡ የምትጸናበትን ፡ የፍርድ ፡ ትእዛዝ ፡ ከዚህ ፡ ዳኛ ፡ ዘንድ ፡ ልናዝዝ ፡ ይገባል ። ቁጥራቸውም ፡ ፲፫ ፡ ትእዛዛት ፡ ናቸው ።

፩ሺ፬፻፲፭ መጀመሪያቸው ፡ ወንድ ፡ እንዲሆን ፡ ነው ። ይህም ፡ የወንድ ፡ እካለ ፡ መጠን ፡ መድረሰን ፡ የፈጸመ ፡ ነው ። አካለ ፡ መጠን ፡ ማድረስም ፡ የጉልምስናን ፡ ሕግ ፡ የፈጸመ ፡ ነው ። ያለዚያስ ፡ አእምሮ ፡ አይደላደልም ። በተላላቆችና ፡ በሽማግሊዎች ፡ በመሰሎቻቸውም ፡ ይፈርድ ፡ ዘንድ፡ ለሹመት ፡ አይበቃም ። እነዚህን ፡ የመሰሉ ፡ ሰዎች ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ባላደረሰው ፡ ዳኛ ፡ ፊት ፡ ይፈርድላቸው ፡ ዘንድ ፡ ሊቆሙ ፡ አይገባም ። በሚረቱት ፡ ላይ ፡ ነገር ፡ አለ ። በሚረቱት ፡ ላይም ፡ ነገር ፡ አለ ።

፩ሺ፬፻፲፮ ስለ ፡ ወንዶችም ፡ ወንድ ፡ ለሴት ፡ ገዥዋ ፡

ሰብእሲት ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ሐዋርያ ፡ ወናትሕኒ ፡ ይደሉ ፡ ለርእስ ፡ እምታሕቲሁ ፡ እስመ ፡ ብእሲ ፡ ክቡድ ፡ ልቡና ፡ ውእቱ ፡ ወሎቱ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይፍታሕ ፡ በከመ ፡ ተነግረ ፡ ውስተ ፡ ቀኖናት ፡ ከመ ፡ ብእሲት ፡ ኢትምሀር ፡ ወኢትኩን ፡ እምኍልቈ ፡ ካህናት ፡ ወፈታሒኒ ፡ ኢይኩን ፡ ዘእንበለ ፡ ካህን ፡፡

፩ሺ፩፻፲፯ ወዳግማዊ ፡ ልብ ፡ ምስለ ፡ አእምሮታቲሁ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ጠባይዕ ፡ እንስሳዊ ፡ ወካልኡኒ ፡ ረባኒዊ ፡ ወአልቦ ፡ ዘይበቍዖ ፡ እንዘ ፡ የኀሥሥ ፡ ወኢየአክሎ ፡ ውስቴቱ ፡ በዘይስቀል ፡ በአንብሮ ፡ ወውእቱ ፡ ከዊኖ ፡ ተላዌ ፡ ለረኪበ ፡ ጸሕቀት ፡ አላ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ዘይጤይቅ ፡ ፍልጠተ ፡ አበይት ፡ ወመናየ ፡ አእምሮ ፡ ርኁቀ ፡ ዕረፍት ፡ ዘይበጽሕ ፡ በትምህርት ፡ ልቡናሁ ፡ ኀበ ፡ ከሢተ ፡ ፍትሕ ፡ ዘንጹብ ፡ ወፍጻሜ ፡ ዘተንብለ ፡ እስመ ፡ በከመዝ ፡ ውእቱ ፡ ይፈትሕ ፡ ማእከለ ፡ ማእምራን ፡ ወእኩያን ፡ ወኢይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ዘየሐጽጽ ፡ እምኔሆሙ ፡ ልበ ፡ ወኢ ፡ ዘይወኅድ ፡ አእምሮ ፡፡

፩ሺ፩፻፲፰ ሣልስ ፡ ይኩን ፡ ምእመነ ፡ አርቶዶክሳዌ ፡ ወካህነ ፡ በትዕይንት ፡፡

፩ሺ፩፻፲፱ ራብዕ ፡ ግብረ ፡ ርትዕ ፡ ዘይደሉ ፡ ለፈታሕያን ፡ ወለሰማዕት ፡ ወተዳግማዊሰ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ምእመነ ፡ ወጠቢበ ፡ ዘርኁቅ ፡ እምንቅፈት ፡ ወድኩን ፡ እምነውር ፡ ህዱእ ፡ ለምሕረት ፡ ወለሥምረት ፡ ተዓጋሤ ፡ በጊዜ ፡ መዓት ፡ ወፈራሄ ፡ እምነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወረትዐ ፡ በሃይማኖቱ ፡ በውስተ ፡ ዓለም ፡፡ እስመ ፡ ዘቦቱ ፡ ሃይማኖት ፡ ወፀቢበ ፡ ርትዕ ፡ ወንጹሕ ፡ ይትከሀሎ ፡ ከመ ፡ ይፍታሕ ፡ ማእከለ ፡ ዕብዳን ፡ ወማእከለ ፡ አንስት ፡ ወላዕለ ፡ ንዋየ ፡ ድኩናን ፡ ወለእለ ፡ ዐለዉ ፡ ታሕተ ፡ ዘይሜግቡሙ ፡ ወዘርኁቀ ፡ እምአድልዎ ፡ ገጽ ፡ ወለዘአጥረየ ፡ ሀድአተ ፡ ወትዕግሥተ ፡ ወኢያስተሐቅሮሙ ፡ ወኢያቀልሎ ፡ ፍትሐታቲሁ ፡ በእንተ ፡ ዘያነብእ ፡ ሎቱ ፡ እምነገር ፡ ዘየሐስዮ ፡፡ ወዳግማዊ ፡ ናሁ ፡ ተነግረ ፡ ውስተ ፡ አንቀጸ ፡ ሰማዕት ፡፡

፩ሺ፩፻፳ ኃምስ ፡ ይኩን ፡ ግዑዘ ፡ እስመ ፡ ዘኢኮነ ፡ ሥሉጠ ፡ ላዕለ ፡ መግቦተ ፡ ነፍሱ ፡ ኢይትከ



ስለሆነ ፡ ነው ። ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ እንደተና ገረ ፡ (ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፳፪) ። ከታችኛው ፡ ይልቅ ፡ ለላይኛው ፡ ፍርድ ፡ ይገባዋል ። ወንድ ፡ አእም ሮው ፡ የጸና ፡ ነውና ፡ ይፈርድም ፡ ዘንድ ፡ ለእ ርሱ ፡ ይገባዋል ። ሴት ፡ እንዳታስተምር ፡ ከካህ ናትም ፡ ቊጥር ፡ እንዳትሆን ፡ በመጻሕፍት ፡ እንደተነገረ ። ዳኛም ፡ ያለካህን ፡ አይሁን ።

፩ሺ፩፻፲፯ ዳግመኛም ፡ ልብ ፡ ከአውቀቶቹ ፡ ጋር ፡ ነው ። (ያለው ፡ መሆን ፡ ነው) ፡ ከእነርሱም ፡ አንዱ ፡ እንስሳዊ ፡ ጠባይዕ ፡ ነው ። ሁለተኛውም ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። ሲሻውም ፡ የሚጠቅመው ፡ የለም ፡ በማኅበር ፡ ወይርሱ ፡ በሚያንጋጥጥ ፡ ገንዘብ ፡ አይበቃም ። ይኸውም ፡ ትጋትን ፡ ለማ ግኘት ፡ የሚከታተል ፡ ሁኖ ፡ ሳለ ፡ ነው ። የፍር ድን ፡ ልዩነት ፡ የሚያውቅና ፡ አእምሮ ፡ ያማረ ለት ፡ ከድንቁርና ፡ የራቀ ፡ በአእምሮውም ፡ መራቀቅ ፡ የጭንቅና ፡ የተሰወረውን ፡ የፍርድ ፡ ፍጻሜ ፡ ወደ ፡ መግለጽ ፡ የሚደርስ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ። በአዋቆችና ፡ በከፋዎች ፡ መካከል ፡ የሚፈርድ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ነውና ፡ ከእነርሱ ፡ ይልቅ ፡ ልቡን ፡ ያጣ ፡ ዕውቀት ፡ የጐደለው ፡ ሊሆን ፡ አይገባም ።

፩ሺ፩፻፲፰ ሦስተኛ ፡ አርቶዶክሳዊ ፡ አማኝና ፡ በአ ርግጥም ፡ ካህን ፡ ይሁን ።

፩ሺ፩፻፲፱ አራተኛ ፡ ለዳኞችና ፡ ለምስክሮች ፡ ቅን ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ የሚገባ ፡ ነው ። መጀመሪ ያው ፡ ግን ፡ የታመነ ፡ ብልህ ፡ ከመነቀፍ ፡ የራቀ ፡ ከነውር ፡ የዳነ ፡ ለምሕረትና ፡ ለመው ደድ ፡ ዝግ ፡ ያለ ፡ በቍጣ ፡ ጊዜ ፡ የሚታገሥ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፡ በዓለሙ ፡ ውስጥ ፡ በሃይማኖት ፡ የቀና ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ። ሃይማኖት ፡ ቅንነትና ፡ ንጽሕናንም ፡ መጠ በቅ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ በአላዋቆችና ፡ በሴ ቶች ፡ መካከል ፡ በደኃ ፡ አደጎች ፡ ገንዘብም በሚያስተዳድራቸውም ፡ ሥር ፡ ሳሉት ፡ ይፈ ርድ ፡ ዘንድ ፡ ይቻለዋልና ። ፊት ፡ አይቶ ፡ ከማ ድላት ፡ የራቀ ፡ ይሁን ። ፀጥታንና ፡ ትዕግሥ ትን ፡ ገንዘብ ፡ ያደረገውን ፡ ሰው ፡ አይናቁት ። ከሚያስቈጣው ፡ ነገር ፡ ወገን ፡ ስለሚመልሱ ለት ፡ ፍርዱን ፡ አያቃልሉ ። ሁለተኛውም ፡ እነሆ ፡ በአንቀጸ ፡ ሰማዕት ፡ ተነግሯል ።

፩ሺ፩፻፳ አምስተኛ ፡ ነፃነት ፡ ያለው ፡ ይሁን ። ራሱን ፡ ለማስተዳደር ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ያልሆነ ፡

አንቀጽ ፡ ፵፫ ።

ሀሎ ፡ ከመ ፡ ይመጣብ ፡ ካልእኒሁ ።

፩ሺ፬፻፷፭ ሳድስ ፡ ይኩን ፡ ድኍነ ፡ ምስማዕ ፡ ወንጹሐ ፡ ከመ ፡ ይፍልጥ ፡ ቃለ ፡ ጽድቅ ፡ ወቃለ ፡ ሐሰት ።

፩ሺ፬፻፷፮ ሳብዕ ፡ ይኩን ፡ ድኍነ ፡ ልሳን ፡ ወዘየአምር ፡ ነገረ ፡ ልሳን ፡ እንተ ፡ ኢትትከሀል ፡ ልሳነ ፡ ሰብእ ፡ ኢመጡ ፡ በዘይትናገሩ ፡ በበይናቲሆሙ ።

፩ሺ፬፻፷፯ ሳምን ፡ ተኀይሎቱ ፡ ይዌ ፡ እንተ ፡ ትከልእ ፡ አብዝኆተ ፡ ሰብእ ፡ ኀቤሁ ፡ በእንተ ፡ ውፉቅድ ፡ ዘከመ ፡ ዝሕጋስ ፡ እስመ ፡ ይትፈቀድ ፡ ከዊነ ፡ ስማዕት ፡ ወተናብሮቱ ፡ በቅድመ ፡ ምኵናኑ ፡ ወአብዝኆ ፡ ሰብእ ፡ እለ ፡ ይትኳነኑ ፡ በኀቤሁ ።

፩ሺ፬፻፷፰ ታስዕ ፡ ይኩን ፡ ማእምረ ፡ ሕግ ፡ ወፍትሐ ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ዘአሥራዊሃ ፡ ወዘአዕጹቂሃ ። አሥራዊሃሰ ፡ ፬ቱ ፡ እሙንቱ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ይኩን ፡ ዘየአምር ፡ ነገረ ፡ መጻሕፍት ፡ አምላካውያት ፡ ወአንብቦቶን ፡ ወተርጓሜቶን ፡ ዘየኀብር ፡ ምስለ ፡ ጥያቄሆን ፡ አእምሮተ ፡ ዘያስተጋብእ ፡ ቦቱ ፡ ጠይቆተ ፡ ዘሀለወ ፡ ውስቴቶን ፡ እምፍትሕ ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ዘተከሥተ ፡ ወዘተተረጐመ ፡ ወዘቀደመ ።

፩ሺ፬፻፷፱ ወካልእኒ ፡ ይለቡ ፡ ነገረ ፡ መጻሕፍት ፡ ውኩፋት ፡ ዘእምቅድመ ፡ ሐዋርያት ፡ ወእምጉባኤ ፡ ወዓዲ ፡ ቃለ ፡ ጉባኤያት ፡ ቅዱሳት ፡ ወዘአበው ፡ ቅዱሳን ፡ ከመ ፡ ይፀመድ ፡ እንከ ፡ ለገቢረ ፡ ቃላቲሆሙ ፡ ወተመስሎ ፡ ምግባራቲሆሙ ፡ ወአእምሮስ ፡ ያበጽሕ ፡ ኀበ ፡ አእምሮተ ፡ ፍትሕ ።

፩ሺ፬፻፸ ወሣልስኒ ፡ ስእመ ፡ አእመረ ፡ ዘኀብሩ ፡ በእንቲአሁ ፡ ተጋብኦተ ፡ ቀኖናት ፡ ወአበው ፡ ማእምራን ፡ ቅዱሳን ፡ ወዘተናፈቁ ፡ ውስቴቱ ፡ ከመ ፡ ይትሉ ፡ እሙንቱ ፡ ወያስተጋድል ፡ ምክንያተ ፡ በእንተ ፡ ዘተፈልጡ ፡ ውስቴቱ ፡ ወየአኀዝ ፡ ዘኮነ ፡ እሙነ ፡ እመክፈልቶቲሁ ፡ ወዘይትረከብ ፡ ኀበ ፡ ተጋብኦ ፡ በእንቲአሁ ።

፩ሺ፬፻፸፩ ራብዕ ፡ አእምሮ ፡ ምዕዳ ፡ ዘያበጽሕ ፡ ቦቱ ፡ ኀበ ፡ አእምሮ ፡ አግብኦተ ፡ አዕጹቅ ፡ እንተ ፡ ትትፈቀድ ፡ ኪያሃ ፡ ዘመስተራምም ፡ በእንቲአሃ ፡ ኀበ ፡ አሥራው ፡ እለ ፡ አሥረው ፡ ኪያሃ ። ወተጋብኦቶሙስ ፡ በእንተ ፡ ትርጓሜሃ ፡ ከመ ፡

ስለ ፡ ዳኛ ።

ሰው ፡ ሊሎቹን ፡ ሊያስተዳድር ፡ አይቻለውምና ፡

፩ሺ፬፻፷፭ ስድስተኛ ፡ ጆሮውና ፡ ዓይኑ ፡ ደኅና ፡ የሆነ ፡ ይሁን ። የዕውነትና ፡ የሐሰት ፡ ቃልን ፡ እንዲለይ ።

፩ሺ፬፻፷፮ ሰባተኛ ፡ እንደበቱ ፡ የረታና ፡ ቋንቋ ፡ የሚያውቅ ፡ ይሁን ። እርስበርሳቸው ፡ በሚነጋገሩ ፡ ገንዘብ ፡ የማትቻል ፡ የሹመቱ ፡ ሰዎች ፡ ቋንቋ ፡ ናት ።

፩ሺ፬፻፷፯ ስምንተኛ ፡ ስለሚያሻው ፡ ነገር ፡ ወደእርሱ ፡ የሰዎችን ፡ መሰብሰብ ፡ ከሚከለክል ፡ ደዌ ፡ መራቅ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ እንደ ፡ ደዌ ፡ ሥጋ ፡ ያለ ፡ ነው ። በሸንጎው ፡ ፊት ፡ የምስክሮችና ፡ የነገረኞች ፡ መኖር ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ የሚፋረዱትን ፡ ሰዎች ፡ ማብዛት ፡ ያስፈልጋልና ።

፩ሺ፬፻፷፰ ዘጠነኛ ፡ ሕግን ፡ የሥሩንና ፡ የቅርንጫፉንም ፡ የክርስቲያንነት ፡ ፍርድ ፡ የሚያውቅ ፡ ይሁን ። ሥሮቹም ፡ አራት ፡ ናቸው ። ከእነርሱም ፡ አንዱ ፡ የቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ ነገር ፡ ንባባቸውንና ፡ ከጥያቄያቸው ፡ ጋር ፡ የሚተባበር ፡ ትርጓሜያቸውን ፡ ከቅጣቶች ፡ ፍርድ ፡ ወገን ፡ አስቀድሞ ፡ የተገለጸውንና ፡ የተተረጐመውን ፡ በውስጡ ፡ ያለውን ፡ መረዳት ፡ የሚሰበስብበት ፡ ዕውቀትንም ፡ የሚያውቅ ፡ ይሁን ።

፩ሺ፬፻፷፱ ሁለተኛም ፡ ከሐዋርያት ፡ ቃልና ፡ ከሥራቸውም ፡ የተነሣ ፡ ተቀባይነት ፡ ያላቸው ፡ የመጻፍትን ፡ ነገር ፡ ዳግመኛም ፡ የቅዱሳት ፡ ጉባኤያትንና ፡ የቅዱሳን ፡ አባቶችን ፡ ቃል ፡ ያስተውል ። ትእዛዛቸውን ፡ ለመሥራትና ፡ በሥራቸውም ፡ ለመምሰል ፡ ፅሙድ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ። ማወቅስ ፡ ፍርድን ፡ ወደማወቅ ፡ ያደርሳል ።

፩ሺ፬፻፸ ሦስተኛውም ፡ የመጻሕፍት ፡ መሰብሰብና ፡ ዐዋቆች ፡ የሆኑ ፡ ቅዱሳን ፡ አባቶች ፡ ስለእርሱ ፡ የተባበሩበትን ፡ በውስጡም ፡ የተለያዩበትን ፡ ቢያውቅ ፡ ነው ፡ እውነተኛውን ፡ ይከተል ፡ ዘንድ ። በውስጡም ፡ ስለተለያዩበት ፡ አስተያየቱን ፡ ይመረምር ፡ ዘንድ ። ከተለያዩበት ፡ እውነተኛ ፡ የሆነውንና ፡ እንደ ፡ ወደሆኑበት ፡ የሚቀርበውን ፡ ይያዝ ።

፩ሺ፬፻፸፩ አራተኛው ፡ ስለእርሷ ፡ ቡቃ ፡ የምትደርግ ፡ የምትወደድ ፡ እዕውቅን ፡ እርሷን ፡ ወደእስተን ፡ ወደአሥራው ፡ መመለስን ፡ ወደማወቅ ፡ የሚያደርስ ፡ ልክን ፡ ማወቅ ፡ ነው ። ስለትርጓሜዋ ፡ መሰብሰባቸው ፡ ግን ፡ በየሁኔታቸው ፡ የሚ

አንቀጽ ፡ ፵፫ ።

ይጺሑ ፡ ፍኖተ ፡ እእምሮ ፡ ዘፍትሐ ፡ ኵነኔ ሆሙ ፡ ለመጻእያን ፡ በበኵነቶሙ ። እስመ ፡ ዘለበወ ፡ አእምሮቶሙ ፡ ለእሉ ፡ ፬ቱ ፡ አሥራው ፡ ይከውን ፡ እምሰብእ ፡ እለ ፡ የአምሩ ፡ ፍትሐ ፡ ወእለ ፡ ያስተሐምሙ ፡ ቦቱ ፡ በፍጻሜ ፡ አበይኖ ፡ ወእለብዎ ፡ ውበዉሕ ፡ ሎቱ ፡ ይረሲ ከመ ፡ ይተርጉም ፡ ወይፍታሕ ፡ ፍትሐ ።

፩ሺ.፱፻፸፰ ዓሥር ፡ ለየእምር ፡ ዘይሠይሞ ፡ ፈታሒ ፡ ዘዐቀበ ፡ እሎንተ ፡ ትእዛዛተ ፡ አመሂ ፡ በዘአቅደመ ፡ አእምሮተ ፡ ግዕዙ ፡ አው ፡ በኅርዮ ፡ አው በሐተታ ፡ ወኅሢሥ ፡ እምእለ ፡ የአምር ፡ ኪያሆሙ ።

፩ሺ.፱፻፸፱ ፲ወ፩ዱ ፡ ዘጸሐፉ ፡ ሎቱ ፡ መጽሐፈ ፡ መባሕት ፡ ለእወፍዮቱ ፡ ኵነኔ ፡ ፍትሕ ፡ ወተፀምዶቱ ፡ ውስቴታ ፡ ወእምዝ ፡ ያግህዱ ፡ ዘንተ ፡ ወያሰምዑ ፡ ሎቱ ።

፩ሺ.፱፻፹ ፲ወ፪ቱ ፡ ቃለ ፡ ምህሮሁ ፡ ሶበ ፡ አወፈይዎ ፡ መጽሐፈ ፡ መባሕት ፡ አመሂ ፡ በንባቡ ፡ አው ፡ በሕገጊሁ ፡ ውስተ ፡ ርእይ ።

፩ሺ.፱፻፹፩ ፲ወ፫ቱ ፡ ኢይክልአዎሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ለእለ ፡ ውስተ ፡ ሢመቱ ፡ አው ፡ ለመብዝኅቶሙ ፡ ለመጺእ ፡ ኀቤሁ ፡ ወኢያእበይ ፡ ኵሉ ፡ ዘውስተ ፡ ሢመቱ ፡ አው ፡ መብዝኅቶሙ ፡ በእንተ ፡ ከመ ፡ ይሠየም ፡ ላዕሌሆሙ ።

፩ሺ.፱፻፹፪ ምስራፍ ፡ ዳግማዊ ፡ በእንተ ፡ ሥርዓቱ ፡ ለአመስከኔ ፡ ኮነት ፡ ሢመቱ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ይከውን ፡ ሥሉጠ ፡ ላዕለ ፡ ሰቡዑ ፡ ኵነኔያት ። አሐቲ ፡ እምኔሆን ፡ ፈሊጠ ፡ ጋእዝ ፡ ወመተረ ፡ ባእስ ፡ አመሂ ፡ በተሳልሞ ፡ ወዕርቅ ፡ እንዘ ፡ ይሣመሩ ፡ አው ፡ በግብር ፡ ፈሪሆሙ ።

፩ሺ.፱፻፹፫ ወካልእትኒ ፡ ካዕበ ፡ አብጽሖተ ፡ ንዋያት ፡ ኀበ ፡ እለ ፡ ይደልዎሙ ፡ ሶበ ፡ ጸንዐት ፡ በእምነተ ፡ አፉሁ ፡ አው ፡ በአጠይቆ ፡ ሰማዕት ።

፩ሺ.፱፻፹፬ ወሣልሲት ፡ ከዊን ፡ አመግቦ ፡ ላዕለ ፡ ዘይክልእዎ ፡ አስተዋዕኦተ ፡ ንዋይ ፡ እመኒ ፡ በእንተ ፡ ናእስ ፡ አው ፡ በእንተ ፡ ሰበዱ ፡ አው ፡ በእንተ ፡ ተማልቆቱ ፡ ከመ ፡ ይትዐቀብ ፡ ንዋዮሙ ፡ በዘይደሉ ፡ ወበእንተ ፡ ጠይቆተ ፡ ፍትሕ ።

፩ሺ.፱፻፹፭ ወራብዒት ፡ በእንተ ፡ አእምሮ ፡ ጊዜያት ፡ ዘቄጺረ ፡ ጕልታት ፡ ለሀቂበ ፡ ሥረዊሃ ፡ ወፈሊጠ ፡ አስጹቂሃ ፡ ወነሢእ ፡ ዘይትረከብ ፡ እም

ስለ ፡ ዳኛ ።

መጡ ፡ የቅጣቶችን ፡ ፍርድ ፡ የማወቅን ፡ ጐዳና ጥርጊያ ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። እሊህን ፡ አራቱን ፡ አሥራው ፡ ማወቅን ፡ ያስተዋለ ፡ ሰው ፡ ፍርድ ፡ ከሚያውቁ ፡ ፍርድንና ፡ ማስተዋልንም ፡ በመፈጸም ፡ ከሚተጉ ፡ ሰዎች ፡ ወገን ፡ ይሆናልና ። እንዲተረጉም ፡ ፍርድም ፡ እንዲፈርድ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ.፱፻፸፰ አሥረኛ ። የሚሾመው ፡ ዳኛ ፡ አስቀድሞ ፡ ጠባዩን ፡ በማወቅ ፡ ወይም ፡ በምርጫ ፡ ወይም ፡ እነርሱን ፡ ከሚያውቃቸው ፡ ሰዎች ፡ በመጠየቅና ፡ በመመርመር ፡ እሊህን ፡ ትእዛዛት ፡ የጠበቀ ፡ መሆኑን ፡ ይጠቅ ።

፩ሺ.፱፻፸፱ ፲፩ኛ ። የፍርድ ፡ ቅጣት ፡ ለመስጠትና ፡ በውስጧም ፡ በሹመቱ ፡ ጸንቶ ፡ ለመኖር ፡ ለማገልገሉ ፡ የመብት ፡ ደብዳቤ ፡ ለጸፉለት ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይህን ፡ ይግለጹለት ። ዓዋጅም ፡ ያናግሩለት ።

፩ሺ.፱፻፹ ፲፪ኛ ። የመብት ፡ ደብዳቤ ፡ በሰጡት ፡ ጊዜ ፡ ንባቡን ፡ ወይም ፡ ሕጉን ፡ በመመልከትም ፡ ቢሆን ፡ የማስተማሩ ፡ ነገር ፡ ነው ።

፩ሺ.፱፻፹፩ ፲፫ኛ ። በሹመቱ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ወይም ፡ ብዙዎችን ፡ ወደእርሱ ፡ ለመምጣት ፡ አይከልክልዋቸው ። በሹመቱ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ወይም ፡ አብዛኛዎቹ ፡ በላያቸው ፡ ስለሚሾምባቸው ፡ እንቢ ፡ አይበሉ ።

፩ሺ.፱፻፹፪ ሁለተኛ ፡ ምዕራፍ ። ስለ ፡ ሥርዓቱ ፡ ይናገራል ። ሹመቱ ፡ በሁሉ ፡ ላይ ፡ ክሆነች ፡ በሰባቱ ፡ ቅጣቶች ፡ ላይ ፡ የሠለጠነ ፡ ይሆናል ። ከእነርሱም ፡ አንዲቱ ፡ በፍቅርና ፡ በዕርቅም ፡ ቢሆን ፡ ተስማምተው ፡ ወይም ፡ በግድ ፡ ፈርተውም ፡ ቢሆን ፡ ፀብ ፡ ክርክርን ፡ ማራቅ ፡ ነው

፩ሺ.፱፻፹፫ ሁለተኛዪቱ ፡ ደግሞ ፡ በአፉ ፡ በማመን ፡ ወይም ፡ በምስክር ፡ በማስረዳት ፡ በጸናች ፡ ጊዜ ፡ ገንዘብን ፡ ለሚገባቸው ፡ ማድረስ ፡ (ማካፈል) ፡ ነው ።

፩ሺ.፱፻፹፬ ሦስተኛዪቱ ። ስለሕፃንነቱ ፡ ወይም ፡ ስለእላዋቂነቱ ፡ ወይም ፡ ስለዋዘኛነቱ ፡ ገንዘቡን ፡ ከማወጣጣት ፡ በሚከለክሉት ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የማስተዳደር ፡ ሁኔታ ፡ ነው ። ገንዘባቸው ፡ በሚገባ ፡ ይጠበቅ ፡ ዘንድ ፡ ፍርዱንም ፡ ስለ ፡ መረዳት ።

፩ሺ.፱፻፹፭ አራተኛዪቱ ። ጉልቶች ፡ የሚቈጠሩበትን ፡ ጊዜያት ፡ ስለማወቅ ፡ ሥሯን ፡ ለመጠበቅና ፡ ጫፏን ፡ ስለመለየት ፡ ከእርሷ ፡ የሚገኘው

ኔሃ ፡ ወእስተዋጽኦቶ ፡ በእንተ ፡ ፍናዋቲሃ ። ወእመኒ ፡ ኮነ ፡ ድልወ ፡ ለአመግቦታ ፡ ይትኖለው ፡ እው ፡ ይሢም ፡ ወእምዝ ፡ ያእምር ፡ እማኅፀንት ፡ ዘሀለወ ፡ ታሕተ ፡ እደዊሆሙ ፡ ለመግብት ፡ ወእምዝ ፡ ግብረ ፡ ደካትም ፡ ወእለ ፡ ሀለዉ ፡ ታሕተ ፡ ምግብና ።

፩ሺ.፬፻፵፯ ኃምሲት ፡ ገቢረ ፡ ትእዛዛት ፡ በከመ ፡ ወሰነ ፡ አዛዚ ፡ ወባቲ ፡ አብሒት ፡ ሕግ ፡ እንበለ ፡ ተከልአ ፡ ወአመሰ ፡ ቦ ፡ ዘአዘዘ ፡ ሎቱ ፡ ኪያሃ ፡ ይኩን ፡ ኖላዌ ፡ ወእመ ፡ አኮ ፡ ይሢም ።

፩ሺ.፬፻፵፰ ሳድሲት ፡ አትልዎ ፡ ለዘይሜኒ ፡ ለፍትሕ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ በምግባር ፡ ዐቢየ ፡ ወኢይከውኖ ፡ ለዘአትለዎ ፡ ለእመ ፡ አትለወ ፡ ካልአ ፡ ዘኢነገረ ፡ ውእቱ ፡ ሎቱ ። ወእምድኅረ ፡ ሞተ ፡ ሥዩም ፡ ዘይበቍዕ ፡ ለሢመተ ፡ ፍትሕ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ግብረ ፡ ዐቢየ ፡ ወአልቦቱ ፡ ሥልጣን ፡ ከመ ፡ ይሢም ፡ ይሠየም ፡ እምነበ ፡ ካልኡ ፡ ዘቦቱ ፡ መባሕት ፡ ለዝንቱ ።

፩ሺ.፬፻፵፱ ሳብዒት ፡ ጥያቄ ፡ ስማዕት ፡ ለይኩኑ ፡ ንጹሓነ እለ ፡ ይከውኑ ፡ ስምዐ ፡ ወእለ ፡ የአምንዎሙ ፡ ወእለ ፡ ኮኑ ፡ ኄራነ ፡ እምላእካኒሁ ፡ ወኅሩይ ፡ ዘእምታሕቴሁ ፡ ከመ ፡ ያንብሮ ፡ ምስለ ፡ ጽንዐት ፡ ወሃይማኖት ፡ ወከመ ፡ ይወልጥ ፡ ሀየንቴሆሙ ፡ እመ ፡ አስተርአዮ ፡ ሀኬት ፡ ወስኢን ፡ ላዕሌሆሙ ።

፩ሺ.፬፻፶ ወለእመሰ ፡ ኮነት ፡ ሢመቱ ፡ እምርት ፡ ዲበ ፡ ፩ዱ ፡ ግብር ፡ ዘእንበለ ፡ ካልኡ ፡ ይከውን ፡ ሕጹጸ ፡ ሢመት ፡ ዘአሁ ፡ ከመ ፡ ዘተሠይመ ፡ ለአውስቦ ፡ ብእሲት ፡ ወአኮ ፡ ላዕለ ፡ ንዋይ ፡ እው ፡ ላዕለ ፡ አሐቲ ፡ ሀገር ፡ ዘእንበለ ፡ አድያሚሃ ፡ ወላዕለ ፡ ፩ዱ ፡ ኅብር ፡ እምሰብእ ፡ ዘእንበለ ፡ ካልአኒሆሙ ፡ በእንተ ፡ ዘአእመረ ፡ ልሳነ ፡ ብሔሮሙ ፡ ወፍጥረቶሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ካልአኒሁ ፡ ወኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይትበደሉ ፡ ዘንቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ዳእሙ ፡ በምግብና ።

፩ሺ.፬፻፶፩ ምዕራፍ ፡ ፫ቱ ፡ በእንተ ፡ ዘይኤዝዝዎ ፡ ቦቱ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ በወንጌል ፡ ቅዱስ ፡ "ኢትፍትሑ ፡ በአድልዎ ፡ አላ ፡ ፍትሐ ፡ ጽድቅ ፡ ፍትሑ ።"

፩ሺ.፬፻፶፩ ድስቅ ፡ ዘ፪ቱ ፡ ወይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡



ንም ፡ ስለመውሰድ ፡ ስለሥራዎቿም ፡ ስለማወጣጣት ፡ ይናገራል ። እርሷን ፡ ለማስተዳደር ፡ የሚገባ ፡ ቢሆን ፡ ይጠብቃት ። ወይም ፡ ይሹም፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከአደራ ፡ ወገን ፡ በሹማምቱ ፡ እጅ ፡ ያለውን ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የድኃ ፡ አደጉንና ፡ በትድድር ፡ ሥር ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ ሥራ ይወቅ ።

፩ሺ.፬፻፵፯ አምስተኛዪቱ ፡ አዛዥ ፡ እንደወሰነ ፡ ትእዛዙን ፡ ማድረግ ፡ ነው ። በእርሷም ፡ ያለመከልከል ፡ ሕግ ፡ አዝዛለች ። እርሷን ፡ ያዘዘለት ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ግን ፡ ጠባቂ ፡ ይሁን ። ይህም ፡ ባይሆን ፡ ይሹም ።

፩ሺ.፬፻፵፰ ስድስተኛዪቱ ፡ በሥራ ፡ ታላቅ ፡ ቢሆን ፡ ለፍርድ ፡ የሚስማማውን ፡ ምክትል ፡ ማድረግ ፡ ነው ። ምክትል ፡ ላደረጉት ፡ እርሱን ፡ ያልነገረለትን ፡ (ያልፈቀደለትን) ፡ ሌላውን ፡ ምክትል ፡ ቢያደርግ ፡ አይገባውም ። ለፍርድ ፡ ሹመት ፡ የሚጠቅም ፡ ዳኛ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ሥራው ፡ ታላቅም ፡ ቢሆን ፡ ሊሾም ፡ ሥልጣን ፡ የለውም። ለዚህ ፡ መብት ፡ ካለው ፡ ከሌላው ፡ ይሾም ፡ እንጂ ።

፩ሺ.፬፻፵፱ ሰባተኛዪቱ ፡ የምስክሮች ፡ ማስረጃ ፡ ናት ። ምስክር ፡ የሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ንጹሐንና ፡ የሚያምኗቸው ፡ ይሁኑ ። ከአገልጋዮቹ ፡ ደጋግ ፡ የሆኑት ፡ ከበታቹ ፡ ያለው ፡ ምርጥ ፡ በሃይማኖት ከመጽናት ፡ ጋር ፡ ያኖረው ፡ ዘንድ ፡ ስንፍና ፡ ድካም ፡ በተገለጠባቸው ፡ ጊዜ ፡ ስለእነርሱ ፡ ይለውጥ ፡ ዘንድ ።

፩ሺ.፬፻፶ ሹመቱ ፡ በሌላው ፡ ሳይሆን ፡ በአንድ ፡ ሥራ ፡ የታወቀች ፡ ብትሆን ፡ ሹመቱ ፡ ጐደሎ ፡ ይሆናል ። በገንዘብ ፡ ያይደለ ፡ ሚስት ፡ ለማግባት ፡ ወይም ፡ በዙሪያዋ ፡ ሳይሆን ፡ በአንዲት ፡ መንደር ፡ ከባልንጀሮቹ ፡ ተለይቶ ፡ ቋንቋቸውንና ፡ ትውልዳቸውን ፡ ስላወቀ ፡ በመላው ፡ ሳይሆን ፡ ከሰዎች ፡ በ፩ ፡ ወገን ፡ እንደተሾመ ፡ ሰው ፡ በሹመት ፡ ቢሆን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ይህን ፡ ሊተላለፍ ፡ አይገባውም ።

፩ሺ.፬፻፶ ሦስተኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ስለሚያዝዙበት ፡ ይናገራል ። ጌታችን ፡ በቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ እውነተኛ ፡ ፍርድ ፡ ፍረዱ ፡ እንጂ ፡ በአድልዎ ፡ አትፍረዱ ፡ አለ ። (ዮሐ ፡ ፯ ፡ ፳፬) ።

፩ሺ.፬፻፶፩ ድስቅ ፡ ፪ ። ቅንና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፈቃድ ፡

ራትዐ ፡ ወተላዌ ፡ ፈቃዱ ፡ ለእግዚአብሔር ።
ዘ፷ቱ ፡ ወነዋ ፡ ተጽሕፈ ፡ ውስተ ፡ መዝሙር ፡
"ወርትዐ ፡ ፍትሑ ፡ አ ፡ ደቂቀ ፡ እጓለ ፡ እመ
ሕያው" ። ዘ፲ቱ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ኢታድሉ ፡ ለገጸ ፡ ባዕል ፡ በውስተ ፡
ፍትሕ ፡ ወኢትምሐሮ ፡ ለነዳይ ፡ እስመ ፡ ለፍ
ትሕ ፡ አልቦ ፡ ውስቴቱ ፡ ምሕረት ፡ ወእእምሩ
ኵነኔ ፡ ኵሎን ፡ ኃጣውእ ፡ ዘዘዚአሃ ፡ ከመ ፡
ኢይኩን ፡ እምኔክሙ ፡ ዐመፃ ፡ ለ፩ዱ ፡ ከመ ፡
ኢይትነሣእ ፡ ላዕሌክሙ ፡ መዓተ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ በእንተ ፡ ፍትሐ ፡ ዐመፃ ፡ ዘእንትሙ ፡
ፈታሕክሙ ፡ ወውእቱ ፡ ይሴእለክሙ ።

፩ሺ.፬፻፶፪ ወተዐተቡ ፡ እምተመስሎ ፡ በረበናት ፡ ዘካህ
ናት ፡ እለ ፡ ኮኑ ፡ ስምዐ ፡ ላዕለ ፡ ሶስና ፡ በባቢ
ሎን ፡ ወፈትሑ ፡ ላዕሌሃ ፡ ፍትሐ ፡ ሞት ፡ በሀ
መፃ ፡ ከመ ፡ ኢትኩኑ ፡ ድልዋነ ፡ ለኵነኔ ፡ እም
ፈታሕት ። እስመ ፡ ለሶስና ፡ አድኀና ፡ እግዚ
አብሔር ፡ እምእደዊሆሙ ፡ ለዐላውያን ፡ ሕግ ፡
በእደ ፡ ዳንኤል ፡ ነቢይ ፡ ወለእልክቱስ ፡ ረበ
ናተ ፡ ካህናት ፡ ቀተሎሙ ፡ በእንተ ፡ ዘአበሱ ፡
ላዕሌሃ ፡ ወወድዮሙ ፡ ውስተ ፡ ኵነኔ ፡ እሳት ።

፩ሺ.፬፻፶፫ ወእግዚአብሔርሰ ፡ የአምር ፡ ፍትሐክሙ ፡
ዘትፈትሑ ፡ ቦቱ ፡ ወኢይትከሀለክሙ ፡ ትጕ
ይእ ፡ እምኔሁ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ርቱዐ ፡ ፍትሕ
ክሙ ፡ ትረክቡ ፡ ለሠናይ ፡ ሠናየ ፡ በርትዕ ፡ እም
ኔሁ ፡ በዝ ፡ ዓለም ፡ ወበዘይመጽእኒ ። ወለእ
መሰ ፡ ኮነ ፡ ፍትሕክሙ ፡ በዐመፃ ፡ ትረክቡ ፡
እኪየተ ፡ ብዙኃተ ።

፩ሺ.፬፻፶፬ ወእአምሩ ፡ ከመ ፡ ፍርሃተ ፡ ገጽ ፡ ይመጽእ ፡
በነሢእ ፡ እምኃ ፡ ወሕልያን ፡ ወትኩኑ ፡ ከማ
ሆሙ ። ይደሉ ፡ ከመ ፡ ኢትትወከፍ ፡ እምኃ ፡
እምእሐዱኒ ፡ ሶበ ፡ ትሁብ ፡ ሢመተ ፡ ዘእንበለ ፡
አምኀበ ፡ ዘእልቦቱ ፡ መባሕት ፡ ዘከመ ፡ ወልድ
ወወላዲ ።

፩ሺ.፬፻፶፭ ወይደልዎ ፡ ከመ ፡ የአዝዞ ፡ ለዘይተልዎ ፡ በዘ
ተአዘዘ ፡ ቦቱ ፡ ውእቱ ፡ ወከመ ፡ የአዝዞሙ ፡
ለላእካኒሁ ፡ ወለመገብቱ ፡ በዮንቴሁ ፡ በፈሪሀ ፡
እግዚአብሔር ፡ ወበአስተሐምሞ ፡ በእንተ ፡
ኀጢአ ፡ ንዋያት ። ወየአዝዞሙ ፡ ለመርዳእያ
ኒሁ ፡ ለምሒክ ፡ በተጻልእ ፡ ወኢይደሉ ፡ ከመ ፡
ይትገበር ፡ ውስተ ፡ መካነ ፡ ምኵናን ፡ ተግ



የሚከተል ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ። ፺ ። በመዝሙ
ርም ፡ እነሆ ፡ ተጽፏል ። የሰው ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፡
እውነት ፡ ፍረዱ ። (መዝ ፡ ፶፰ ፡ ፩) ። ፲ ፡ ዳግ
መኛም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ። በፍ
ርድ ፡ ጊዜ ፡ ለባለጸጋ ፡ ፊት ፡ አታድላ ። ለድኃ
ውም ፡ አትዘንለት ፡ አለ ፡ በፍርድ ፡ ውስጥ ፡
ምሕረት ፡ የለምና ። (ዘሌ ፡ ፲፱ ፡ ፲፭) ። ከእናንተ
በአንዱ ፡ ላይ ፡ በደል ፡ እንዳይሆን ፡ የኀጢአቶ
ችን ፡ ሁሉ ፡ ፍርድ ፡ በየራሷ ፡ እወቁ ። እናንተ ፡
በፈረዳችሁት ፡ የዓመፅ ፡ ፍርድ ፡ የእግዚአብሔ
ር ፡ መዓት ፡ በላያችሁ ፡ እንዳይመጣ ፡ እርሱም ፡
ይጠይቃችኋል ።

፩ሺ.፬፻፶፪ በባቢሎን ፡ በሶስና ፡ ላይ ፡ የሐሰት ፡ ምስክ
ሮች ፡ የሆኑና ፡ በዓመፅ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ የፈረ
ዱባትን ፡ የካህናት ፡ መምህራንን ፡ ከመምሰል ፡
ተጠበቁ ። ከዳኞች ፡ ለቅጣት ፡ ዝግጁዎች ፡ እን
ዳትሆኑ ። እግዚአብሔር ፡ ሶስናን ፡ በነቢይ ፡
ዳንኤል ፡ ቃል ፡ ከሕግ ፡ አፍራሾች ፡ እጅ ፡ አድ
ኗታልና ። እነዚህን ፡ የካህናት ፡ መምህራንን ፡
ግን ፡ በእርሷ ፡ ላይ ፡ ስለበደሉ ፡ ገደላቸው ።
ወደእሳት ፡ ቅጣትም ፡ ጨመራቸው ። (ተረ ፡
ዳን ፡ ፶፰ ፡ ፷፩) ።

፩ሺ.፬፻፶፫ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ የምትፈርዱትን ፡
ፍርድ ፡ ያውቅባችኋል ። ከእርሱም ፡ ልትሸሸጉ ፡
አትችሉም ። ፍርዳችሁ ፡ የቀና ፡ ቢሆን ፡ በእው
ነት ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ በዚህም ፡ ዓለም ፡ በሚመ
ጣውም ፡ ዓለም ፡ መልካም ፡ ዋጋ ፡ ታገኛላችሁ ።
ፍርዳችሁ ፡ በዓመፅ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ፍዳ ፡
ታገኛላችሁ ።

፩ሺ.፬፻፶፬ ፊት ፡ አይቶ ፡ ማድላት ፡ እጅ ፡ መንሻንና ፡
መማለጃን ፡ በመቀበል ፡ እንደሚመጣ ፡ እወቁ ።
እንደ ፡ እነርሱም ፡ ትሆናላችሁ ። ሹመት ፡ በስ
ጠኸው ፡ ጊዜ ፡ ካንድ ፡ ሰው ፡ እንኳ ፡ እጅ ፡
መንሻ ፡ እንዳትቀበል ፡ ይገባል ። መብት ፡ ከሌ
ለው ፡ ዘንድ ፡ ቢሆን ፡ ነው ፡ እንጂ ። ይኸውም ፡
እንደ ፡ ልጅችና ፡ እንደ ፡ አባት ፡ ያለ ፡ ነው ።

፩ሺ.፬፻፶፭ ምክትሉን ፡ እርሱ ፡ በታዘዘበት ፡ ሊያዝዘው ፡
አገልጋዮችንና ፡ ሹማምቱንም ፡ እግዚአብሔ
ርን ፡ በመፍራትና ፡ ገንዘብን ፡ ስለመሻት ፡ በመ
ትጋት ፡ ስለእርሱ ፡ ፋንታ ፡ ሊያዝዛቸው ፡ ይገ
ባል ። ረዳቶቹንም ፡ በጠብ ፡ ጊዜ ፡ ስመራራት
ይዘዛቸው ። በሸንጎው ፡ ቦታ ፡ መገበያየት ፡
ወይም ፡ መሻረክ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ የሚመስለው

አንቀጽ : ፵፫ ።

ይቡ : ወኢ : ተሳትፎ : ወኢ : ዘይመስሎ : ለገዛንቱ : ኢ : ለነፍሱ : ወኢ : ለመጋቢሁ : ዘለዉቅ : ሎቱ : ወከመ : ኢይትወከፍ : ፩ዱ : እምተጸላእያን : ዘእንበለ : በዓለ : ዕዳሁ : ወኢ : እምድኅረ : ተፈልጦቶሙ ።

፩ሺ፩፻፵፯ ምዕራፍ : ራብዕ : በእንተ : ትእዛዛተ : ፍትሑ ። ይደልዎ : ቅድመ : ከመ : ያስተርኢ : መጽሐፈ : ሢመቱ : ወይትነበብ : በውስተ : መካነ : ምዙናን : ከመ : ይስማዕ : ዜናሁ : ወእምዝ : ያዕርጉ : ሎቱ : ነገረ : ምክንያቶሙ : ለሙቁሓን : ወለዕለ : ሀለዉ : በግዞት : ይፍታሕ : ለዘይደልዎ : ፍትሐት : እምኔሆሙ : ወይኅድግ : ለዘኢይደልዎ : ፍትሐት ። ወእመኒ : በእንተ : ተአምኖቱ : ወበስምዕ : ዘኮነ : ሎቱ : አው በእንተ : አበይዖ : ላዕሌሁ ።

፩ሺ፩፻፵፰ ወስዘኒ : ይቤ : ግፉዕ : እነ : ወኢሀለወ : በዓለ : ዕዳሁ : ከመ : የሐድስ : ተኳንኖቶ : ይጽሐፍ : መልእክተ : ኀበ : በዓለ : ዕዳሁ : ከመ : ይብጻሕ : ለተኳንኖ : ለእመ : ሀለወ : በመካን : ቅሩብ : ወለእመ : ተድኅረ : ይፍትሖ : ወይፈንዎ : እምድኅረ : ወሀበ : ትሕቢተ ። ወለዘሂ : ተጠየቀ : ከመ : ነዳይ : ውእቱ : ይንሣእ : እምኔሁ : ተሓባዬ : ከመ : ይፍትሖ : እስከ : አመ : ይረክብ : ዘይፈዲ : ሎቱ : ዘተለቅሐ ። ወእምዝ : የእዝዞሙ : ለላእካኒሁ : ከመ : ኢያብኡ : ኀቤሁ : ዕድወ : ዘእንበለ : እድዉ : ወኢያቅድሙ : በዓለ : ዕዳ : እምበዓለ : ዕዳሁ : ወኢ : ለዘተድኅረ : እምነ : ዘቀደመ ።

፩ሺ፩፻፵፱ ወይደሉ : ሎቱ : ከመ : ይኩን : ሀዱእ : ወኢ ተዓባዬ : ወኢይፍታሕ : እንዘ : ቦቱ : ዘያማስኖ : ለሕሊናሁ : ዘከመ : ቍጥዓ : ወፍርሃት : መሀውካን ። ወዘከመ : ኀዘን : ወፍሥሓ : መርስዓን : ወዘከመ : ረኃብ : ወጽምእ : ነካይያን : ወዘከመ : ደዌ : ወሕማም : አሕማምያን ። ወዘከመ : ንዋም : ወድቃስ : መዋዕያን : ወዘከመ : ሀኬት : ወድካም : አሕማምያን : ወበስካርኒ : ወቅላሌ : ወተእንትሎ : እምብዝኀ : ፈቲሐ : ፍትሕ ። ወኢይደልዎ : ሎቱ : ከመ : ይሠውር : ዘእንበለ : ጊዜያት : ለሰረፍት : ወለገቢረ : መፍቅዳት ።

፩ሺ፩፻፶ ወእምከመ : በጽሑ : ኀቤሁ : ተጻላእያን :

ስለ : ዳኛ ።

ለራሱ : ወይም : ለታወቀው : ሹሙ : ሊደረግ : አይገባም ። ከጠበኞች : ሰዎች : አንዱን : ያለባላጋራው : ወይም : ከተለያዩ : በኋላ : ሊቀበል : አይገባም ።

፩ሺ፩፻፵፯ ፩ኛ : ምዕራፍ : ስለፍርዱ : ትእዛዛት : ይናገራል ። አስቀድሞ : ወሬው : ይሰማ : ዘንድ : የሹመቱ : ደብዳቤ : በአደባባይ : ሊታይና : ሊነበብ : ይገባል ። ከዚህ : በኋላ : የታሠሩትን : ሰዎችና : በግዞት : ያሉትን : ሰዎች : ምክንያት : ነገር : ይንገሩት ። በእርሱ : ሥልጣን : ሊፈታ የሚገባውን : ይፍታ ። መፈታት : የማይገባውን ያቆየው ። ስለመታመኑና : ስለ : ተመሰከረለት : ወይም : ስለተፈረደበት : ቢሆን ።

፩ሺ፩፻፵፰ ክርክሩን : ያድስ : ዘንድ : ባላጋራው : በሌለበት : እኔ : ተበድያለሁ : ቢል : ወደ : ባላጋራው : ደብዳቤ : ይጻፍ ። በቅርብ : ቦታ : ካለ : ለመፈራረድ : ይደርስ : ዘንድ ። ቢቀር : ዋስ : ከለጠ : በኋላ : ፈትቶ : ይሰደደው ። ደኃ : እንደሆነ : ለታወቀ : ሰው : የተበደረውን : የሚከፍልበት : እስኪያገኝ : ድረስ : ከእርሱ : ዋስ : ይቀበል ። ከዚህ : በኋላ : አጋፋሪዎቹን : ባላጋራውን : ከባላጋራው : ለይተው : ወደእርሱ : እንዳያስገቡ : ባለዕዳን : ከባለዕዳው : የኋለኛውንም : ከቀደመው : እንዳያስቀድሙ : ይዘዛቸው ።

፩ሺ፩፻፵፱ ፀጥ : ያለ : የማይታበይ : ይሆን : ዘንድ : ይገባዋል ። አሳቡን : የሚለውጥ : ነገር : እያለበት : አይፍረድ ። ይኸውም : እንደሚያውኩ : እንደ : ቁጣና : እንደ : ፍርሃት : እንደሚያዘነጉ : እንደ : ኀዘንና : እንደ : ደስታ : እንደሚነኩ : እንደ : ረኀብና : እንደ : ፅምዕ : እንደሚያሳምሙ : እንደ : ደዌና : እንደ : ሕማም : ድል : እንደሚነሡ : እንደ : እንቅልፍና : እንደ : ሽልብታ : እንደሚያሳዝኑ : እንደስንፍናና : እንደ : ድካም : ያሉ : ናቸው ። በስካርና : በመቅለል : ፍርድን : ከመፍረድ : ብዛት : የተነሣም : በመሰልቸት : አይፍረድ ። ለዕረፍትና : ፈቃድን : ለመፈጸም : በተወሰነው : ጊዜ : ካልሆነም : በቀር : ሊሰወር : አይገባውም ።

፩ሺ፩፻፶ የተጣሉ : ሰዎች : ወደእርሱ : ከመጡ : ፳ማረ

አንቀጽ ፡ ፵፫ ።

ይውዋን ፡ በቀዳማዊ ፡ ዘቀደመ ፡ ወኢይቅድሞ ፡ ለዘይነግሮ ፡ እምውስተ ፡ ብዙኃን ፡ እምፍትሐት ፡ አሐቲ ፡፡ ወእመበ ፡ እመስተባእሳን ፡ እለ ፡ ጸመዉ ፡ ወእለሂ ፡ በሐዊረ ፡ ፍኖት ፡ አው ፡ በደዌ ፡ ዘተዳደቆሙ ፡ ወያስተዓሪ ፡ ማእከለ ፡ መስተባእሳን ፡ በበዊእ ፡ ወበነቢር ፡ ወበተወክፎሂ ፡ ወአስምዖ ፡ ኀቢሮሙ ፡ ወተናግሮ ፡ ሎሙ ፡ ወአርትዖ ፡ ውስተ ፡ ፍትሕ ፡ ሎሙ ፡ ወላዕለ ሆሙ ፡ ወኢያሌዕልስ ፡ ምስለ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔ ሆሙ ፡ ወኢያሀበ ፡ ምክንያተ ፡ ወኢይትበአስ ፡ ወኢያመክኖ ፡ ቦቱ ፡ እመኒ ፡ ኮነ ፡ ጽኑዐ ፡ አው ፡ ድኩመ ፡ አው ፡ ንኡስ ፡ ወክቡረ ፡ ከመ ፡ ኢይ ምስሎ ፡ ለክቡር ፡ ዘይፈርህዎ ፡ ወኢኀዳዩ ፡ ወጽ ኑስ ፡ ከመ ፡ ኢይትበጾ ፡ ርትዐ ፡ ዘእሁ ፡ ወኢ ያስተደኅን ፡ ግቢረ ፡ ፍትሕ ፡ እምከመ ፡ ተጋ አዙ ፡ መስተባእሳን ፡ በእንበለ ፡ በማብር ፡ ጽኑዕ

፩ሺ፬፻፶ ወኢይፍታሕ ፡ ለርእሱ ፡ ወኢ ፡ ለአሐዱ ፡ እም ወላድያኒሁ ፡ ወኢ ፡ ለእምኑቢ ፡ ወውሉዱ ፡ ወውሉደ ፡ ውሉዱ ፡ ወኢ ፡ ለአኀዊሁ ፡ ወብእ ሲቱ ፡ ምስለ ፡ ካልእኒሆሙ ፡፡ ወይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይፍታሕ ፡ ለካልእ ፡ ምስለ ፡ ካልእ ፡ ወከመ ፡ ይፍታሕ ፡ ሎሙ ፡ ምስለ ፡ ካልእኒሆሙ ፡ ለእመ ፈቀዱ ፡ መስተባእሳን ፡ ወይከውኖ ፡ እንከ ፡ ከመ ፡ ይእበዮ ፡፡ ወባሕቱ ፡ እሉ ፡ ይትኃነኑ ፡ ምስለ ፡ ካልእኒሆሙ ፡ ኀበ ፡ መጋቤሁ ፡ ወኢ ይከውኖ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ስምዐ ፡ በእንቲ አሆሙ ፡፡ ወኢይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይፍታሕ ፡ ለጸ ላኢሁ ፡ ወላዕሌሁ ፡ ካዕበ ፡ ወኢይደልዎ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ስምዐ ፡ በላዕሌሁ ፡ እስመ ፡ ግብ ረት ፡ ዘፍትሕ ፡ ክሡታት ፡ እሙንቱ ፡ ወግብረ ፡ ከዊን ፡ ስምዕ ፡ ኅብእት ፡ ይእቲ ፡፡

፩ሺ፬፻፶፩ ወእምከመ ፡ ፈትሐ ፡ ፍትሐ ፡ ለ፩ዱ ፡ ወእ ምዝ ፡ ተሐደሰ ፡ እምሳሊሁ ፡ ዘከማሁ ፡ ይደ ልዎ ፡ ከመ ፡ ይፍታሕ ፡ ቦቱ ፡ በዘያበጽሕ ፡ ጸሐፎ ፡ ኀቤሁ ፡ በውእቱ ፡ ጊዜ ፡ ወእመኒ ፡ ኢነበረ ፡ ምስለ ፡ ፍትሑ ፡ ዘቀደመ ፡ ረትዐ ፡ ከማሁ ፡ እምሳሊሁ ፡፡ ወኢያብጥል ፡ ፍትሐ ፡ ነፍሱ ፡ ወኢ ፡ ፍትሐ ፡ ካልኡ ፡ ዘእንበለ ፡ ለእመ ፡ ወለጠ ፡ ነገረ ፡ ሕገዊ ፡ ዘኢነበረ ፡ ምስለ ፡ ቃለ ፡ ሕግ ፡ ገሃደ ፡ አው ፡ በትርጓሜ ፡ አው ፡ በትእዛዘ ፡ ቀኖናት ፡ ዘተጋብኡ ፡ በእ

ስለ ፡ ዳኛ ።

በሆነው ፡ በፊተኛው ፡ ሰው ፡ ይጀምር ። በአን ዲት ፡ ፍርድ ፡ ኋለኛውን ፡ ከብዙዎች ፡ እያስቀ ድመው ። ከተጣሉት ፡ ሰዎች ፡ መንገድ ፡ በመ ሄድም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ድንገት ፡ ባገኛቸው ፡ ደዌ ፡ የደከሙ ፡ ቢኖሩ ፡ በተጣሉ ፡ ሰዎች ፡ መካ ከል ፡ በመግባትና ፡ በመቀመጥ ፡ በመቀበልና ፡ ወደ ፡ እነሱም ፡ በማዳመጥ ፡ እነርሱንም ፡ በማነ ጋገር ፡ ለእነሱም ፡ ፍርድን ፡ በማቅናት ፡ ትክ ክለኛ ፡ ይሁን ። ከእነርሱም ፡ ከአንዱ ፡ ጋራ አያሾክሹክ ፡ (ቆይታ ፡ አያድርግ) ። ምክንያ ትም ፡ አይስጠው ፡ አይጣለውም ። ብርቱ ወይም ፡ ደካማ ፡ ወይም ፡ ደኃ ፡ ባለጸጋም ቢሆን ፡ አያመካኝበት ። ባለጸጋውን ፡ የሚፈ ሩት ፡ እንዳይመስለው ። ደኃና ፡ ችግረኛም በፍርዱ ፡ ተስፋ ፡ እንዳይቆርጡ ። የተጣሉት ከተከራከሩ ፡ በኋላ ፡ ጽኑ ፡ ችግር ፡ ካልሆነ በቀር ፡ ፍርድ ፡ መስጠትን ፡ ወደኋላ ፡ አይበል ።

፩ሺ፬፻፶ ለራሱ ፡ ከወላጆቹም ፡ ስአንደኛው ፡ ወይም ፡ ለአያቱ ፡ ስልጆቹ ፡ ስልጅ ፡ ልጆቹም ፡ ወይም ፡ ለወንድሞቹ ፡ ለሚስቱም ፡ ከሌሎች ፡ ጋራ ፡ አይፍረድ ። ስሌላው ፡ ከሌላው ፡ ጋራ ፡ የተጣሉ፡ ሰዎች ፡ ከወደዱ ፡ ከሌሎች ፡ ጋራ ፡ ይፈርድላ ቸው ፡ ዘንድ ፡ ይገባዋል ። እንቢ ፡ ሊልም ፡ እን ግዲህ ፡ ይገባዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ እነርሱ ፡ ከሌ ሎች ፡ ጋራ ፡ ከሹሙ ፡ ዘንድ ፡ ይፋረዱ ። ስለነር ሱም ፡ ምስክር ፡ ሊሆን ፡ አይገባውም ። ዳግመ ኛም ፡ በጠላቱ ፡ ላይ ፡ ሊፈርድ ፡ አይገባውም ። በእርሱም ፡ ምስክር ፡ ሊሆን ፡ አይገባውም ። የፍርድ ፡ ሥራዎች ፡ ግልጾች ፡ ናቸውና ። የምስ ክርነት ፡ ሁኔታ ፡ ሥራ ፡ ግን ፡ የተሰወረች ፡ ናትና ።

፩ሺ፬፻፶፩ ለአንዱ ፡ ፍርድ ፡ ቢፈርድ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እንደዚሁ ፡ የመሰለ ፡ ቢታደስ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ አሳቡን ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡ በሚያደርስ ፡ ገንዘብ ፡ ሊፈርድበት ፡ ይገባዋል ። በመጽሐፍ ፡ ከቀደ መው ፡ ፍርዱ ፡ ጋራ ፡ ምንም ፡ ባይተባበር ፡ ምሳሌው ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። የራሱን ፡ ፍርድ ፡ ወይም ፡ የሌላውን ፡ ፍርድ ፡ አይለውጥ ። ከሕግ ቃል ፡ ጋራ ፡ የማይተባበር ፡ ሕጋዊ ፡ ነገርን ፡ በግልጽ ፡ ወይም ፡ በትርጓሜ ፡ ወይም ፡ አባቶች ገንዘብ ፡ ባደረጉት ፡ እውቀት ፡ ስለእነርሱ ፡

ንቲአሆን ፡ አበው ፡ በአእምሮ ፡ ዘአጥረይዎ ፡ አው ፡ ዘይመስሎ ፡ ለልቡናሁ ፡ አእምሮ ፡ እስመ ፡ ተመይጦተ ፡ ርትዕ ፡ ይኄይስ ፡ እምተ፡ን ልፎ ፡ ላዕለ ፡ ቃል ፡ ዕሩቅ ። ወይፈትሕ ፡ በዘተ ግህደ ፡ እምቃል ፡ እሙን ፡ ውስተ ፡ መንበረ ፡ ፍትሕ ፡ ለእመ ፡ ተጠየቀ ፡ አእምሮቱ ፡ በኀ ቤሁ ፡ ወበኀበ ፡ ተአማኒ ፡ አው ፡ በዘተከሠተ ፡ በሰማዕት ፡ ለእመ ፡ ቆመ ፡ አው ፡ መሐላ ፡ ለእመ ፡ ደለወ ፡ ወኢይፈትሕ ፡ ላዕለ ፡ ዘኢየአ ምሮ ፡ ዘእንበለ ፡ ግጸዌ ።

፩ሺ.፩፻፶፱ ምዕራፍ ፡ ኃምስ ። በእንተ ፡ መሐላ ፡ ይቤ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ዕብ ፡ ፮፥ ፡ "ወመሐላሰ ፡ ዘይምሕል ፡ ሰብእ ፡ በዘውእቱ ፡ የዐቢ ፡ እም ኔሁ ፡ ይምሕል ፡ ወኵሉ ፡ ኃእዝ ፡ ዘትከውን ፡ ማእከሌሆሙ ፡ ትትፌጸም ፡ በመሐላ ። ወበእ ንተ ፡ ውእቱ ፡ ፈድፋደ ፡ አፍቀረ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ከመ ፡ ያርኢ ፡ ለወራስያነ ፡ ተስፋ ፡ ከመ ፡ ተስፋሁ ፡ ኢየዐሉ ፡ ወአጽንዖ ፡ በቃለ ፡ መሐላ" ። ወሶበ ፡ ኢዘሎ ፡ ምንትኒ ፡ ዘየዐቢ ፡ እምኔሁ ፡ ከመ ፡ ይምሐል ፡ ቦቱ ፡ መሐለ ፡ በር እሱ ፡ ወይቤ ፡ እነ ፡ ባርኮ ፡ እባርከከ ፡ ወአብ ዝኆ ፡ አስተባዝኀከ ። ወቃለ ፡ እግዚእነ ፡ ዘው ስተ ፡ ወንጌል ፡ ዘይቤ ፡ ኢትምሐሉ ፡ ግሙራ ፡ ወአኮ ፡ ዘይቤ ፡ በእንተ ፡ ተፋትሖታት ፡ አላ ፡ ይቤ ፡ በእንተ ፡ ተናግሮ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ፈጸመ ፡ ዘንተ ፡ ቃለ ፡ በቃሉ ፡ ዘይብል ፡ ለት ኩን ፡ ቃልክሙ ፡ እመኒ ፡ እወ ፡ እወ ፡ ወእመኒ ፡ አልቦ ፡ እልቦ ። ወይቤ ፡ ካዕበ ፡ ዘተወሰከሰ ፡ ላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ እምእኩይ ፡ ውእቱ ። ወተወስ ኮሰ ፡ ይእቲ ፡ እንተ ፡ ኢይትፈቀድ ፡ ኀቤሃ ፡ ወከ ዊነ ፡ መሐላሰ ፡ በጊዜ ፡ ኃእዝ ፡ ናሁ ፡ ይትፈ ቀድ ፡ በበይነ ፡ ግብር ፡ ወባሕቱ ፡ ይደሉ ፡ ለሰ ብእ ፡ ከመ ፡ ኢይምሐል ፡ በዘይትከሀሎ ፡ ይቤዙ ፡ መሐላሁ ፡ በንዋዩ ፡ ወዘእንበለ ፡ ንዋዩ ፡ በእንተ ፡ ሰበየ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባሕ ቲቱ ፡ ወበእንተ ፡ ዘይሴፎ ፡ ዘሀሰወ ፡ ኀቤሁ ።

፩ሺ.፩፻፷ ወይቤ ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈወርቅ ፡ በው ስተ ፡ ትርጓሜ ፡ ዝንቱ ፡ ቃል ፡ ወእመ ፡ ትቤ ፡ ምንት ፡ ይእቲ ፡ መሐላ ፡ እንተ ፡ የኀሥሥ ፡ ወይ መጽእ ፡ ወይሁብ ፡ ፅዱ ፡ እምኔነ ፡ ለቢጹ ፡ በጊዜ ፡ ፈቀደ ፡ ኪያሃ ፡ እቤ ፡ በፈሪሀ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ይእቲ ። ወዘሂ ፡ ይገብር ፡ በሕገ ፡ ትእ



በተሰበሰበ ፡ በመጻሕፍት ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ ለል ቡናው ፡ በመሰለው ፡ ሕጋዊ ፡ ነገርን ፡ ካልለ ወጠ ፡ በቀር ፡ ወደማይጠቅም ፡ ነገር ፡ ከመተላ ለፍ ፡ ይልቅ ፡ ወደ ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ መመለስ ፡ ይሻላልና ፡ እወቅ ። በፍርድ ፡ አደባባይ ፡ ከታ መነው ፡ ቃል ፡ የተነሣ ፡ በተገለጸለት ፡ ገንዘብ ፡ በእርሱና ፡ በታማኙ ፡ ዘንድ ፡ እውቀቱ ፡ ቢረጋ ገጥ ፡ ወይም ፡ በምስክሮቹ ፡ በተገለጸው ፡ ነገር ፡ ቢጸና ፡ ወይም ፡ መሐላ ፡ የሚገባው ፡ ቢሆን ፡ ይፍረድ ። በማያውቀውም ፡ ላይ ፡ ሳይለይ ፡ አይ ፍረድ ።

፩ሺ.፩፻፶፱ ፭ኛው ፡ ምዕራፍ ፡ ስለመሐላ ፡ ይናገራል ። ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ዕብ ፡ ፮ ። መሐላስ ፡ የሚምል ፡ ሰው ፡ ከእርሱ ፡ በሚበ ልጥ ፡ ይምላል ። በመካከላቸው ፡ የምትደረግ ፡ ክርክር ፡ ሁሉ ፡ በመሐላ ፡ ትፈጸማለች ። ስለዚ ህም ፡ ተስፋ ፡ ለሚወርሱ ፡ ተስፋውን ፡ እንዳያ ስቀር ፡ ይገልጽ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጽሞ ወደደ ። በመሐላ ፡ ቃልም ፡ አጸናው ። ይምልበ ትም ፡ ዘንድ ፡ ከእርሱ ፡ የሚበልጥ ፡ ምንም ፡ ስለሌለ ፡ መባረክን ፡ እባርክሃለሁ ፡ መባዛትንም እበዛሃለሁ ፡ ብሎ ፡ በራሱ ፡ ማለ ። (ዕብ ፡ ፮ ፡ ፲፫ - ፲፰) ። ጌታችንም ፡ በወንጌል ፡ ከቶ ፡ አትማሉ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ስለመፋረድ ፡ አይደለም ። ስለ መናገር ፡ ተናገረ ፡ እንጂ ። ይህንን ፡ ትእዛዝ ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ ቃላችሁ ፡ እውነቱን ፡ እውነት ፡ ሐሰቱን ፡ ሐሰት ፡ ትሁን ፡ በሚል ፡ ቃሉ ፡ ፈጽ ሞታልና ። ዳግመኛም ፡ በዚህ ፡ ላይ ፡ የተጨመ ረውስ ፡ ከክፉ ፡ የተገኘ ፡ ነው ፡ አለ ። (ማቴ ፡ ፭ ፡ ፴፬ - ፴፯) ። በእርሷ ፡ ላይ ፡ መጨመርስ ፡ የማ ትፈለግ ፡ ናት ። በክርክር ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ የመሐላ ሁነታ ፡ በግልጽ ፡ ያስፈልጋል ። ነገር ፡ ግን ለሰው ፡ መሐላውን ፡ በገንዘብ ፡ ወይም ፡ ያለገን ዘብ ፡ ማስቀረት ፡ በሚቻለው ፡ ሁናቴ ፡ ስለእግ ዚአብሔር ፡ ገናናነት ፡ ብቻ ፡ በእርሱም ፡ ያለ ውን ፡ ተስፋ ፡ ስለሚያደርግ ፡ እንዳይምል ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ.፩፻፷ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅም ፡ ይህን ፡ ቃል በተረጐመበት ፡ አንቀጽ ፡ እንዲህ ፡ አለ ። መሐ ላ ፡ ምንድር ፡ ናት ? ፡ ብትል ፡ ከእኛ ፡ አንዱ ፡ በጓደኛው ፡ ላይ ፡ እርሷን ፡ በወደደ ፡ ጊዜ ፡ የሚ ሻት ፡ የሚያመጣት ፡ የሚሰጣት ፡ መሐላ ፡ እግ ዚአብሔርን ፡ በመፍራት ፡ ናት ፡ እላለሁ ። የመ

አንቀጽ ፡ ፶፫ ።

ዘዛት ፡ መሢሒሐውያት ፡ ኢይፈቅድ ፡ መሐላ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ይከውን ፡ በኀበ ፡ ሰብእ ፡ ፍሩሀ ፡ ወእግዚእብሔር ፡ ይከውኖ ፡ ረዳኤ ።

፭ሺ.፩፻፶፬ በስ ፡ ፪ቱ ፡ ኢትምሐል ፡ በስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ግብር ፡ ዕሩቅ ፡ ወፈድፋደሰ ፡ በሐሰት ፡ ወናሁ ፡ እዘዘነ ፡ ከመ ፡ ኢንምሐል ፡ በካልእ ፡ እምትእዛዛተ ፡ መጻሕፍት ፡ እላ ፡ ሰእመ ፡ ኮነ ፡ በግብር ፡ ንምሐል ፡ በእንቱ ፡ ሕጸተ ፡ እእምሮቶሙ ፡ ለሰብእ ፡ ወእኮ ፡ ዘእንበለ ፡ ፍርሀተ ፡ እግዚእብሔር ፡ ከመ ፡ ኢንትኮነን ፡ በመሐላ ፡ ዘምሉእ ፡ ፍርሀተ ። ዘ፰ወ፰ቱ ፡ ወእመቦ ፡ እምኊልቈ ፡ ካህናት ፡ ዘይምሕል ፡ በስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሐሰት ፡ ይሰደድ ፡ ፫ተ ፡ ዓመተ ፤

፭ሺ.፩፻፶፭ መክ ፡ ፶ወ፰ቱ ፡ ፻፰ወ፯ቱ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ማእከለ ፡ ፪ቱ ፡ እደው ፡ ተሰናእዎት ፡ በተግባር ፡ እው ፡ ተሳትፎት ፡ እው ፡ ኪዳን ፡ ወጸሐፉ ፡ ማእከሌሆሙ ፡ መጽሐፈ ፡ ጥዩቀ ፡ ለአጽንዖ ፡ መሐላ ፡ ዘማእከሌሆሙ ፡ ከመ ፡ ውንቶሙ ፡ ኢይገብእ ፡ እምዘተሰነእዉ ፡ ቦቱ ። ወለእመ ፡ ገብአ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ እምነ ፡ ዘተጽሕፈ ፡ ይገሥጽ ፡ መኰንን ፡ በእንተ ፡ መሐላሁ ፡ በሐሰት ፡ ወይደልዎ ፡ ይግበር ፡ ዘሀለወ ፡ ጽሑፈ ፡ በመጽሐፍ ። መ፳ ፡ ፳ወ፩ዱ ፡ ወዘሂ ፡ ፈትሐ ፡ ላዕሌሁ ፡ መኰንን ፡ ከመ ፡ ይምሐል ፡ ወእንበረ ፡ እዴሁ ፡ ላዕለ ፡ ወንጌል ፡ ቅዱስ ፡ ወመሐለ ፡ ቦቱ ፡ ወእምዝ ፡ ተከሥተ ፡ ሐሰቱ ፡ ይትገሠጽ ።

፭ሺ.፩፻፶፮ ክፍል ፡ አእምር ፡ ከመ ፡ እምላካዊት ፡ ሕግ ፡ ናሁ ፡ ትፈቅድ ፡ ሥነ ፡ ምግባሬት ፡ በእግህዶ ፡ ርትዕ ፡ በጥንተ ፡ ቀዳሚ ፡ ሕግ ፡ እምገዘ ፡ ቊመቱ ፡ ግብራት ፡ ኀብእት ፡ ወገቢር ፡ በውስቱ ፡ ሕግ ፡ ደኀሪ ፡ ወነዋ ፡ ነበረ ፡ ተከልአ ፡ በውስቱ ፡ ሕግ ፡ ብሊት ፡ እመሐላ ፡ በሐሰት ፡ ወከመ ፡ ይትገሠጽ ፡ ዘወድቀ ፡ ቦቱ ። ወመሐላሰ ፡ በውስቱ ፡ ሕግ ፡ ሐዲስ ፡ በፍትሐ ፡ ልቡና ፡ ውእቱኬ ፡ ከመ ፡ ኢይንብቡ ፡ ቦቱ ፡ ግሙራ ፡ በእንቱ ፡ ዘይቤ ፡ እግዚእነ ፡ በወንጌል ፡ "ተብሀለ ፡ ለቀደምትክሙ ፡ ኢተሐሰዉ ፡ ውስቱ ፡ መሐላ ፡ ወእንሰ ፡ እብለክሙ ፡ ኢትምሐሉ ፡ ግሙራ" ።

ስለ ፡ ዳኛ ።

ሢሕን ፡ የትእዛዛት ፡ ሕግንም ፡ የሚሠራ ፡ መሐላን ፡ አይሻም ። እርሱ ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ የተፈራ ይሆናልና ። እግዚአብሔርም ፡ ረዳት ፡ ይሆነዋልና

፭ሺ.፩፻፶፬ በስ ፡ ፪ ። በተርታ ፡ ነገር ፡ ይልቁንም ፡ በሐሰት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ አትማል ። ከመጻሕፍትም ፡ ትእዛዝ ፡ ወጥተን ፡ በሌላ ፡ [illegible]ዳን ምል ፡ እነሆ ፡ አዝዞናል ። በሰዎች ፡ እውቀተ ፡ ማነስ ፡ በግድ ፡ እንድንምል ፡ ቢሆን ፡ ነው ፡ እንጂ ። ፍርሃትን ፡ በተመላ ፡ መሐላ ፡ እንዳይፈረድብንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያለመፍራት ፡ አይሁን ። ፳፰ ። ከካህናት ፡ ወገን ፡ በሐሰት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የማለ ፡ ቢኖር ፡ ፫ ፡ ዓመት ፡ ይለይ ።

፭ሺ.፩፻፶፭ መክ ፡ ፶፰ ፡ ፻፳፯ ። በሁለት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የሥራ ፡ ስምምነት ፡ ወይም ፡ ሽርክነት ፡ ወይም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ቢኖር ፤ በመካከላቸውም ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ለማጽናት እነርሱ ፡ ከተሰማሙበት ፡ ውል ፡ እንዳይመለሱ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ደብዳቤ ፡ በመካከላቸው ፡ ቢጻጻፉ ፡ ከእነርሱም ፡ አንዱ ፡ ከተጻፈው ፡ ውል ፡ ቢመለስ ፤ በሐሰት ፡ ስለመማሉ ፡ ዳኛ ፡ ይቅጣው ። በመጽሐፍ ፡ ተጽፎ ፡ ያለውንም ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ይገባዋል ። መ፳ ፡ ፳፩ ። ዳኛ ፡ እንዲምል ፡ የፈረደበትም ፡ ሰው ፡ እጁንም ፡ በቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ ላይ ፡ ጭኖ ፡ ቢምልበት ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሐሰቱ ፡ ቢገለጽ ፡ ይቀጣ ።

፭ሺ.፩፻፶፮ ክፍል ። እነሆ ፡ የእምላክ ፡ ሕግ ፡ በመጀመሪያው ፡ ሕግ ፡ መሠረትነት ፡ ርትዕን ፡ በመግለጽ፤ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተሠወረች ፡ ሥራ ፡ በመጽናት ፡ በኋለኛውም ፡ ሕግ ፡ በመሥራት ፡ የምግባራትን ፡ ደግነት ፡ እንደምትወድ ፡ እወቅ ። እነሆ ፡ በብሉይ ፡ ሕግም ፡ በሐሰት ፡ ከመማል ፡ መከልከል ፡ እንዲገባ ፡ የወደቀበትም ፡ እንዲቀጣ ፡ ተጽፏል ። (ዘዳ ፡ ፭ ፡ ፲፩) ። በሐዲስ ፡ ሕግ ፡ ግን ፡ በልቡና ፡ ፍርድ ፡ መሐላ ፡ ከቶ ፡ የማይናገሩት ፡ ነው ። ጌታችን ፡ በወንጌል ፡ ከእናንተ ፡ በፊት ፡ ለነበሩት ፡ ሰዎች ፡ በሐሰት ፡ አትማሉ ፡ የተባለውን ፡ ሰምታችኋል ፣ እኔ ፡ ግን ፡ ከቶ ፡ አትማሉ ፡ እላችኋለሁ ፡ ስባል ፡ ነው ። (ማቴ ፡ ፭ ፡ ፴፫ - ፴፯)

፩ሺ፬፻፶፯ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ በግብር ፡ አው ፡ ዘእንበለ ፡ ግብር ፡ እመ ፡ አኮ ፡ ለእመ ፡ ይከውን ፡ ዘተበ ሀለ ፡ በአእምሮ ፡ ወእስተማሰሎ ፡ በእንተ ፡ ዘተብህለ ፡ ቀዳሚ ፡ ይኩን ፡ ከማሁ ፡ ወዳግማ ዊኒ ፡ ወውእቱ ፡ መሐላ ፡ ዘይከውን ፡ ውስተ ፡ ቃላት ፡ ላዕለ ፡ ፍኖተ ፡ ስሒት ፡ ወርስዐት ፡ በእ ንተ ፡ እከዮ ፡ ዘልማድ ፡ ዘከመ ፡ ወዲቅ ፡ ውስተ ካልኣት ፡ ግብራት ፡ በአእምሮ ፡ ወዘእንበለ ፡ አእምሮ ፡ ወፈድፋደሰ ፡ ዘእንበለ ፡ ተሐዝቦ ፡ እንዘ ፡ ኢይፈቅድ ፡ ይደሉ ፡ ላዕሌሁ ፡ ንስሓ ፡ ለእመኒ ፡ መሐለ ፡ በጽድቅ ፡ አው ፡ በሐሰት ።

፩ሺ፬፻፶፰ ወቀዳሚሰ ፡ እመኒ ፡ ቦ ፡ ከመ ፡ ይትመሰል ፡ በመሐላ ፡ ዘመን ፡ ዘኀለፈ ፡ ወበዘይመስሎ ፡ ዘውእቱ ፡ እግዚአብሔርሃ ፡ ከመ ፡ ኢገበርኩ ፡ አው ፡ ገበርኩ ፡ አው ፡ አልብከ ፡ ኀቤየ ፡ አው ፡ ሊተ ፡ ኀቤከ ። ወእመአኮ ፡ ለእመ ፡ ይትሜሰል ፡ በዘመን ፡ ዘይመጽእ ፡ ወእምሳሊሁ ፡ የአምር ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ኢይገብር ፡ ወእመሂ ፡ እገብር ። ተመስሎሰ ፡ በኀላፊ ፡ ይትከፈል ፡ ኀበ ፡ ፪ቱ ፡ አክፋል ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ምስለ ፡ አእምሮ ፡ ጥዩቅ ፡ እንዘ ፡ ሕሊ ናሁ ፡ የኀብር ፡ ምስለ ፡ ቃሉ ፡ ወለዝንቱሰ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይብዝኁሙ ፡ በዕርቅ ፡ ለእመ ፡ ተከሀለ ። ወለእመ ፡ ኢተከሀለ ፡ ይከውን ፡ ኀጢአቱ ፡ ላዕለ ፡ ዘአምሐሎ ፡ ለእመ ፡ አእመረ ፡ ግኑዐ ፡ ዚአሁ ፡ ወሕሊናሁ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘኢ ተዓቀቢ ፡ ለዘላዕሌሁ ፡ ግብር ፡ ውስተ ፡ ነፍሱ ፡ ለእመ ፡ አእመረ ፡ መሐሊ ፡ በውእቱ ፡ ይለም ፡ ዝኒ ፡ ኀበ ፡ አሚን ፡ ወእስተሐምሮ ፡ እምእግ ዚአብሔር ፡ ወእመሰ ፡ ኮነ ፡ ዘየኀብር ፡ ለሀ ልም ፡ ኢይደልም ፡ ዕዳ ፡ ምንትኒ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘይትሐዘብ ፡ ሎቱ ፡ ሕሊናሁ ።

፩ሺ፬፻፶፱ ወዳግሚትኒ ፡ ለእመ ፡ ይከውን ፡ ምስለ ፡ አእምሮ ፡ ሐሰት ፡ ወውእቱ ፡ ስልጡተ ፡ ቀል ፡ እምሕሊና ። ወዝንቱ ፡ ይደሉ ፡ ኀዲጎቱ ፡ ሎቱ ፡ በእንተ ፡ ቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በው ስተ ፡ ኦሪት ፡ ዘይብል ፡ ኢትምሐል ፡ በስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጣሪከ ፡ በሐሰት ፡ ወለእመ ፡ ወድቀ ፡ በውከት ፡ እምሰይጣን ፡ ይደልዎ ፡ ገቢእ ፡ እምኔሁ ፡ ኀበ ፡ አሚን ፡ ወእምዝ ፡ ኀበ ፡ ንስሓ ።

፩ሺ፬፻፷ ወሣልስቲትኒ ፡ ለእመ ፡ ይከውን ፡ ምስለ ፡ ስሒት ፡ ወዝንቲኒ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይትባዘው ፡

፩ሺ፬፻፶፯ በግድ ፡ ወይም ፡ ያለግድ ፡ ቢሆን ፡ ያም ፡ ባይ ሆን ፡ የተባለው ፡ ነገር ፡ በዕውቀት ፡ ወይም ፡ በማስመሰል ፡ ቢሆን ፡ መጀመሪያ ፡ ስለተነገረ ፡ እንደዚያው ፡ ይሁን ። ሁለተኛውም ፡ በመሳትና በመርሳት ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ስለልማድ ፡ ክፋት በቃል ፡ የሚሆን ፡ መሐላ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ በዕውቀት ፡ በአለማወቅም ፡ ቢሆን ፡ በሌሎች ፡ ሥራዎች ፡ እንደ ፡ መውደቅ ፡ ያለ ፡ ነው ። ይል ቁንም ፡ ያለጥርጥር ፡ ሳይወድ ፡ በእውነት ፡ ወይም ፡ በሐሰት ፡ ቢምል ፡ ለእርሱ ፡ ንስሓ ይገባዋል ።

፩ሺ፬፻፶፰ መጀመሪያ ፡ ግን ፡ ባለፈው ፡ ዘመን ፡ መሐላ ፡ በሚመስለውም ፡ ይመስል ፡ ዘንድ ፡ ቢኖር ፡ ይኸውም ፡ እንዳላደረግሁ ፡ ወይም ፡ እንዳደ ረግሁ ፡ ወይም ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ገንዘብ ፡ እንዳ ለህ ፡ ወይም ፡ በአንተ ፡ ዘንድ ፡ ገንዘብ ፡ እንዳለ ኝ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማለት ፡ ነው ። ያም ፡ ባይ ሆን ፡ በሚመጣው ፡ ዘመን ፡ በሚመስለውም ፡ ቢመስል ፡ እንዳላደርገው ፡ ወይም ፡ እንዳደር ገው ፡ እግዚአብሔር ፡ ያውቃል ፡ ማለት ፡ ነው። ባለፈው ፡ መመስልስ ፡ በ፪ ፡ ይከፈላል ። ከእነር ሱም ፡ አንዱ ፡ ሐሳቡ ፡ ከቃሉ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ሁኖ ፡ በዕውቀት ፡ እርግጠኛ ፡ ቢሆን ፡ እንዲዘ ፡ ያለውን ፡ ቢቻል ፣ በዕርቅ ፡ ሊያድኑት ፡ ይገ ባል ። ባይቻል ፡ ግን ፡ በደሉ ፡ በማለው ፡ ላይ ፡ ይሆናል ። በደሉንም ፡ ቢያውቅ ፡ ሐሳቡም ፡ በሥራው ፡ ለራሱ ፡ የማይጠበቅ ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ይህንን ፡ ቢያውቅ ፡ ወደ ፡ ማመንና ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ወደሚገኝ ፡ ይቅርታ ፡ መመ ለስ ፡ ተገባው ። ለመኖር ፡ የሚስማማ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ዕዳ ፡ አይገባውም ። ሕሊናው የሚጠራጠርበት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ።

፩ሺ፬፻፶፱ ሁለተኛዪቱም ፡ ሐሰት ፡ ከዕውቀት ፡ ጋራ ፡ ቢሆን ፡ ያህም ፡ ከሐሳብ ፡ የተነጣ ፡ የቃል ፡ ሽን ገላ ፡ ነው ። ይህንም ፡ ሊተዉት ፡ ይገባል ። እግዚአብሔር ፡ በኦሪት ፡ በፈጣሪህ ፡ በእግዚአብ ሔር ፡ ስም ፡ በሐሰት ፡ አትማል ፡ ብሎ ፡ ስለተ ናገረ ፡ (ዘጸ ፡ ፳ ፡ ፲፩) ። ከሰይጣን ፡ የተነሣ ፡ በመታወክ ፡ ቢወድቅ ፡ (ቢምል) ፡ ከዚህ ፡ ወደ ማመን ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ንስሐ ፡ መመ ለስ ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ፬፻፷ ሦስተኛዪቱም ፡ በስሕተት ፡ ቢሆን ፡ ያህም ፡ በሚታገሥበት ፡ አስቀድመን ፡ ከተናገርነው ፡

ብስርቅ ፡ ዘይትዔገሥ ፡ ቦቱ ፡ ወዘይበዝኅ ፡ እም ሥንየ ፡ ዘአቅደምነ ፡ ዘከርናሁ ፡ ወለእመ ፡ ኢተ ከሀለ ፡ ጌጋዩ ፡ ላዕለ ፡ አምሓሊ ፡ ለእመ ፡ አእ መረ ፡ ማዕዖ ፡ እሙ ፡ ተስሕተ ፡ ውስቴቱ ። ወተ ዩቅስ ፡ በዘይመጽእ ፡ እስመ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ጽድቅ ፡ ውስቴቱ ፡ ዘኢይከውን ፡ አበሳ ፡ ደለወ እንከ ፡ ሎቱ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ አበሳ ፡ ይፀውር ደለወ ፡ ገቢአ ፡ እምኔሁ ፡ ወተመስሎሰ ፡ በዘይ መጽእ ፡ ለእመ ፡ አልቦቱ ፡ ቃል ፡ እሙን ፡ ኢይ ደሉ ፡ ዘእንበለ ፡ ከመ ፡ ይፀመዱ ፡ ኪያሁ ። ወእ መሰ ፡ ቦቱ ፡ እሙን ፡ ቃል ፡ ደለዎ ፡ ከመ ፡ ይኅ ድግዎ ፡ ወንስሓሰ ፡ ለዘከማሁ ፡ ከመ ፡ ኢይወ ስክ ፡ ዲበ ፡ አበሳሁ ፡ በቃል ፡ ኃጢአተ ፡ ዘገቢር

፩ሺ.፬፻፳፩ አእምር ፡ ከመ ፡ ቃለ ፡ መሐላ ፡ ውእቱ ፡ መሐላ ፡ በስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአልቦ ፡ ፍል ጠት ፡ ማእከለ ፡ እሉ ፡ ፪ቱ ፡ ማእከለ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወስመ ፡ ክርስቶስ ፡ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ለለ፩ዱ ፡ እምነ ፡ እሉ ፡ ፪ቱ ፡ አስማት ፡ ስመ ፡ አምላክ ፡ ውእቱ ፡ ስመ ፡ ክርስቶስ ፡ አም ላክ ፡ ውእቱ ፡ ዘተሰብአ ። ወለዘፈቀደ ፡ ይትሉ ፡ ዘንተ ፡ ለተገርሞ ፡ ወለእፍርሆ ፡ በምንትኒ ፡ እምአስማቲሁ ፡ እለ ፡ ዝኩራት ፡ በመጻሕፍት ፡ እምላካውያን ፡ ይከውኖ ፡ ሎቱ ፡ ውእቱ ፡ በእምሳል ፡ ከመ ፡ ዘይብል ፡ እግዚአብሔር ፡ ዐቢይ ፡ ወኀያል ፡ ከሃሊ ፡ ማእምር ፡ ዘኀቡእ ፡ ወዘገሃድ ፡ ዘይፈድዮ ፡ ለኵሉ ፡ ለለ፩ዱ ፡ በከመ፡ ምግባሩ ፡ ዘኢያነጽሖ ፡ ለዘመሐለ ፡ ስሞ ፡ በሐ ሰት ፡ ወመሐላስ ፡ ዘእንበለ ፡ በእንግዚአብሔር ፡ ወበንገራቲሁ ፡ ወበእሊአሁ ፡ ኢይደሉ ፡ ወእሊ አሁስ ፡ ዘከመ ፡ ወንጌሉ ፡ ወመስቀሉ ፡ ወታ ቦቱ ወቅዱሳኒሁ ። ወኢይደሉ ፡ እምሕሎቱ ለዘጠፍአ ፡ ልቡ ፡ ወለዘኢያብጽሖ ፡ አካለ ፡ መጠን ።

፩ሺ.፬፻፳፪ ሥርዋጽ ፡ ወለዝንቱ ፡ ቃል ፡ ቦቱ ፡ ኅሥሣ ፡ እስመ ፡ መሐላ ፡ ዘበእግዚአብሔር ፡ ይከውን ፡ እምኔሁ ፡ መሐላ ፡ በክርስቶስ ፡ ወኢይትዌለጥ ፡ እስመ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ይትበሀል ፡ ኀበ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወስመ ፡ ክርስቶስኒ ፡ ይትበሀል ፡ ኀበ ፡ ስመ ፡ ወልድ ፡ ባሕቲቱ ።

፩ሺ.፬፻፳፫ ምስራፍ ፡ ፯ቱ ፡ በእንተ ፡ መንበረ ፡ ፍትሕ ፡



ከደግ ፡ ነገር ፡ ወገን ፡ በሚበዛ ፡ ዕርቅ ፡ ሊበኸር ፡ ይገባል ። ባይቻል ፡ ግን ፡ በደሉ ፡ በአማዩ ፡ ላይ፡ ነው ። በደሉን ፡ ቢያውቅ ፡ ወይም ፡ በውስጡ ፡ ቢሳሳት ። እርግጠኛውስ ፡ በሚመጣው ፡ ነው ። በውስጡ ፡ በደል ፡ የማይሆን ፡ እውነት ፡ ቢሆን፡ እርሱን ፡ መያዝ ፡ ይገባናልና ። በደሉን ፡ የሚሸ ከም ፡ ቢሆንም ፡ ከእርሱ ፡ መመለስ ፡ ተገባ ። በሚመጣውም ፡ መምሰል ፡ የታመነ ፡ ቃል ፡ ባይኖረው ፡ ሊያፈርሱት ፡ እንጂ ፡ ሊፈጽሙት ፡ አይገባም ። እውነት ፡ ቃል ፡ ቢኖርበት ፡ ግን ፡ ሊተዉት ፡ ተገባ ። ንስሓም ፡ ለእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ነው ። በነቢብ ፡ ኃጢአት ፡ ላይ ፡ የገቢር ፡ ኃጢ አት ፡ እንዳይጨምር ።

፩ሺ.፬፻፳፩ የመሐላ ፡ ቃል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ መማል ፡ እንደሆነ ፡ እወቅ ። በእግዚአብሔር ፡ ስምና ፡ በክርስቶስ ፡ ስም ፡ በእኒህ ፡ በሁለቱ ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ የለም ። ከእኒህ ፡ ከሁለቱ ፡ ስሞች ፡ ሁሉ ፡ ለእያንዳንዱ ፡ የእምላክ ፡ ስም ፡ ነውና ። ክርስቶስ ፡ የሚለው ፡ ስም ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡ አምላክ ፡ ነው ። ለማስፈራራትና ፡ ለማስ ገረም ፡ በቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ከተነገሩት ፡ ስሞቹ ፡ በማናቸውም ፡ ይሆን ፡ ሊከታተል ፡ ቢወድ ፡ ለእርሱ ፡ ይገባዋል ። ለምሳሌ ፡ ገናና ፡ ኀያል ሁሉን ፡ ቻይ ፡ የተሰወረውንና ፡ የተገለ ጸውን ፡ የሚያውቅ ፡ ለእያንዳንዱ ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ የሚከፍል ፡ በሐሰት ፡ በስሙ ፡ የማለ ውን የማያነፃ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይወቀብኝ እንደማለት ፡ ነው ። መሐላም ፡ በእግዚአብሔር፡ በነገሮቹና ፡ በወገኖቹ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አይገ ባም ። ወገኖቹም ፡ እንደ ፡ ወንጌሉ ፡ እንደ ፡ መስቀሉና ፡ እንደ ፡ ታቦቱ ፡ እንደ ፡ ቅዱሳኖ ቹም ፡ ያሉት ፡ ናቸው ። አእምሮዉ ፡ የጠፋ ውንና ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያላደረሰውን ፡ ማማል ፡ አይገባም ።

፩ሺ.፬፻፳፪ ሥርዋጽ ። በዚህ ፡ ቃል ፡ ምርምር ፡ አለበት ። በእግዚአብሔር ፡ የተማለው ፡ መሐላ ፡ ከእርሱ ፡ የተነሣ ፡ በክርስቶስ ፡ መማል ፡ ይሆናልና ። አይለወጥምም ። ክብር ፡ ይግባውና ፡ እግዚአብ ሔር ፡ የሚለው ፡ ስም ፡ ለአብ ፡ ለወልድ ፡ ለመ ንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይነገራልና ። ክርስቶስ ፡ የሚ ለውም ፡ ስም ፡ ለወልድ ፡ ስም ፡ ብቻ ፡ ይነገ ራል ።

፩ሺ.፬፻፳፫ ሰባተኛው ፡ ምስራፍ ፡ ስለፍርድ ፡ አደባባይ ፡

ወእለ ፡ ይበጽሑ ፡ ኀቤሁ ፡ ወእለሂ ፡ ኢይበጽሑ ድስቅ ፡ ፲ቱ ፡ ለየሀልዉ ፡ ምስሌክሙ ፡ ኤጲስ ቆጶሳት ፡ በመንበረ ፡ ፍትሕ ፡ ቀሳውስት ፡ ወዲ ያቆናት ፡ ወፍትሑ ፡ ዘእንበለ ፡ አድልዎ ፡ በር ትዕ ፡ ከመ ፡ ሰብእ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወእእምሩ ፡ ከመ ፡ ክርስቶስ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሀልው ፡ ውእቱ ፡ ምስሌክሙ ፡ በሀውደ ፡ ፍትሕ ፡ ከመ ፡ ይርእይ ፡ ዘትፈትሑ ፡ ቦቱ ፡ ወይሰማዕ ፡ ዘትትናገሩ ፡ ቦቱ ፡ ወናሁ ፡ ይቤ ፡ በውስተ ፡ ሕግ ፡ ኢትኅበር ፡ ምስለ ፡ ብዙኃን ለገቢረ ፡ እከይ ፡ ወኢትትወከፍ ፡ ነገረ ፡ ፅሩዐ ፡ ወኢትንበር ፡ ውስተ ፡ ማኅበርሙ ፡ ለእለ ፡ ያፀርው ፡ ጽድቀ ።

፩ሺ፩፻፳፩ ክፍል ፡ ወይደሉ ፡ ከመ ፡ ያስተዳልዉ ፡ ለፈታሕት ፡ ምንባረ ፡ ንጹሐ ፡ ወጽሩየ ፡ ኀበ ፡ ኢይለክፎሙ ፡ ቍር ፡ ወኢሐሩር ፡ ወኢጺእት ፡ በውስቲታ ፡ ወኢይንበሩ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በምሥዋዕ ፡ ለፈቲሐ ፡ ፍትሕ ፡ እስመ ፡ በዊእ ፡ ኀበ ፡ ምሥዋዕ ፡ ኢ.ብውሕ ፡ ዘእንበለ ፡ ለካህናት ፡ ከመ ፡ ይባኡ ፡ ወኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ውስቴቱ ፡ ተባእሶ ፡ ወክሳሕ ። ወመፍትው ፡ ከመ ፡ የሀልዉ ፡ ኀቤሁ ፡ ማእምራን ፡ ወእለ ፡ ይከውኑ ፡ ስምዐ ፡ ከመ ፡ ሶበ ፡ ተዳደቆ ፡ ጠዋይ ፡ ነገር ፡ ከመ ፡ ይትማከር ፡ ምስሌሆሙ ፡ በእንቲአሁ ። ወለእመኒ ፡ ኢተ ጠየቀ ፡ ፈቲሐ ፡ ፍትሕ ፡ ያስተድኅር ፡ ኪያሁ ፡ እስከ ፡ ይጤየቅ ።

፩ሺ፩፻፳፪ ምስራፍ ፡ ፯ቱ ። በእንተ ፡ ጊዜያተ ፡ ፍትሕ ፡ ወከዋኔሁ ። መከ ፡ ፬ ፡ ኢይሥርዑ ፡ መኳንንት ፡ በምንትኒ ፡ እምሥርዓታቲሆሙ ፡ በዕለተ ፡ እሑድ ፡ ወኢያፍርሁ ፡ በውስቴቱ ፡ ሰብእ ፡ ኢ ፡ በዓለ ፡ ስዳ ፡ ወኢ ፡ መኰንን ፡ ወኢ ፡ ሐራ ፡ ወኢ ፡ መጸብሐዊ ።

፩ሺ፩፻፳፫ ድስቅ ፡ ፲ቱ ፡ ወይኩን ፡ ተጋብእትክሙ ፡ በእንተ ፡ ፍትሕክሙ ፡ እምዕለተ ፡ ሰኑይ ፡ ወለ እመ ፡ ሀለወ ፡ ሀየ ፡ ተጋእዞ ፡ ፍልጡ ፡ ኪያሃ ፡ ወኩኑ ፡ ዕሩቃነ ፡ በዝንቱ ፡ ኑኅ ፡ ይእቲ ፡ ሰሙን ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ሰንበት ፡ ከመ ፡ ትትፈጸም ፡ ነገረ ፡ ተባእሶ ። ወበዕለተ ፡ እሑድ ፡ ቅድስት ፡ ትከውኑ ፡ እንከ ፡ ዘዓሁ ፡ እስተሳለም ክሙ ፡ ማእከለ ፡ ተጻላእያን ፡ ወእምከመ ፡ በጽሑ ፡ ኀቤክሙ ፡ ተጻላእያን ፡ ይቲሙ ፡ ክል ኤሆሙ ፡ በቅድሜክሙ ፡ ማእከለ ፡ መንበረ ፡



ወደእርሱ ፡ ስለሚደርሱና ፡ ስለማይደርሱ ፡ ይና ገራል ። ድስቅ ፡ ፲ ። ኤጲስቆጶሳት ፡ ሆይ ፡ ከፍ ርድ ፡ ሸንጎ ፡ ቀሳውስትና ፡ ዲያቆናት ፡ ከእና ንተ ፡ ጋር ፡ ይኑሩ ። የእግዚአብሔርም ፡ ሰዎች ፡ እንደመሆናችሁ ፡ ያለ ፡ አድልዎ ፡ በእውነት ፡ ፍረዱ ። የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ክርስቶስ ፡ የምትፈርዱትን ፡ ሊያይ ፡ የምትናገሩትንም ሊሰማ ፡ በፍርድ ፡ አደባባይ ፡ ከናንተ ፡ ጋር ፡ እንዳለ ፡ እወቁ ። እነሆ ፡ በመጽሐፍ ፡ ክፋትን ፡ ለመሥራት ፡ ከብዙዎች ፡ ጋራ ፡ አትተባበር ፡ የማይረባ ፡ ነገርንም ፡ አትቀበል ፡ እውነትን ፡ በማይናገሩ ፡ ሰዎች ፡ ስብሰባ ፡ ውስጥም ፡ አት ቀመጥ ፡ ተብሏል ። (ሚሪ ፡ ፮ ፡ ፲፪) ።

፩ሺ፩፻፳፩ ክፍል ፡ ብርድና ፡ ሐሩር ፡ ክፉ ፡ ሽታም ፡ ከማያገኛቸው ፡ ንጹሕና ፡ ጥሩ ፡ መቀመጫ ፡ ለዳኞች ፡ ሊያዘጋጁ ፡ ይገባል ። በሚሠዋበት በቤተክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ፍርድ ፡ ለመፍረድ ፡ አይቀመጡ ። ወደ ፡ ምሥዋዕ ፡ መግባት ፡ ከካህ ናት ፡ በቀር ፡ ሌሎች ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ አይገባ ምና ። ጠብና ፡ ጩኸት ፡ በውስጡ ፡ ሊሆን ፡ አይገባም ። አዋቂዎችና ፡ ምስክር ፡ የሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ጠማማ ፡ ነገር ፡ ባጋጠመው ፡ ጊዜ ፡ ስለእርሱ ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ እንዲማከር ፡ ከእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ሊኖሩ ፡ ይገባል ። ፍርዱም ፡ ያልተረዳው ፡ ቢሆን ፡ እስኪረዳው ፡ ድረስ ፡ ያቆይ ።

፩ሺ፩፻፳፪ ሰባተኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ስለፍርድ ፡ ጊዜያትና ፡ ስለሁኔታው ፡ ይናገራል ። መከ ፡ ፬ ። መኳንንት በዕለተ ፡ እሑድ ፡ ከሥርዓታቸው ፡ ወገን ፡ ከም ንም ፡ አይሥሩ ። በዚያም ፡ (በእሑድ ፡ ቀን) ፡ አበዳሪና ፡ ዳኛ ፡ ጭፍራና ፡ ቀራጭም ፡ ሰውን ፡ አያስፈራሩ ።

፩ሺ፩፻፳፫ ድስቅ ፡ ፲ ። ስለፍርዳችሁ ፡ መሰብሰባችሁ ፡ ከሰኞ ፡ ጀምሮ ፡ ይሁን ። ከዚያም ፡ ክርክር ፡ ቢኖ ር ፡ እርሱን ፡ ለዩ ። በዚህ ፡ በዚህች ፡ ሳምንት ፡ ርዘመትም ፡ እስከ ፡ ቅዳሜ ፡ ድረስ ፡ ከነገር ፡ ተለዩ ። የበጣ ፡ ነገር ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ። በከበ ረች ፡ በዕለተ ፡ እሑድም ፡ እነሆ ፡ በተጣሉት ፡ መካከል ፡ አስታራቂዎች ፡ ትሆናላችሁ ። የተጣ ሉ ፡ ሰዎችም ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ቢደርሱ ፡ እንደ ሕጉ ፡ ባህል ፡ በፍርድ ፡ ሸንጎ ፡ መካከል ፡ ሁለ ቱም ፡ በፊታችሁ ፡ ይቁሙ ። የጥላቸውንም ፡

ፍትሕ ፡ ከመ ፡ ባህለ ፡ ሕግ ፡ ወእምከመ ፡ ሰማ ዕክሙ ፡ ቃለ ፡ ተጻልአቶሙ ፡ ፍትሑ ፡ ማእከሌሆሙ ፡ በጽድቅ ፡ ወበርትዕ ፡ ወኢትፍትሑ ፡ በቃለ ፡ ፩ዱ ፡ ሰድው ፡ ዘእንበለ ፡ ይብጻሕ ፡ በዓለ ፡ ዕዳሁ ፡ እላ ፡ ሶበ ፡ ይትራከቡ ፡ ፪ሆሙ ፡ ተጻላእያን ፡ ፍትሑ ፡ ማእከሌሆሙ ፡ በርትዕ ። ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኅሥዋ ፡ ለጽድቅ ፡ ወፍትሑ ፡ ባቲ ፡ ወሶበ ፡ ትነብሩ ፡ ለኰንኖ ፡ እንዘ ፡ ተጻላእያን ፡ ይትኳነኑ ፡ በቅድሜክሙ ፡ ገጸ ፡ በገጽ ፡ ኢትስምዕዮሙ ፡ አኮ ፡ እስከ ፡ ይኅብሩ ፡ ዕርቀ ፡ ወሥረዩ ፡ ዕዳሆሙ ፡ በጽድቅ ።

ነገር ፡ ከሰማችሁ ፡ በኋላ ፡ በመካከላቸው ፡ በእውነትና ፡ በቅን ፡ ፍረዱ ። ባላጋራው ፡ ሳይመጣ በ፩ ፡ ባላጋራ ፡ ቃል ፡ አትፍረዱ ። ሁለቱ ፡ ተከራካሪዎች ፡ በተገናኙ ፡ ጊዜ ፡ በመካከላቸው በቅን ፡ ፍረዱ ፡ እንጂ ። እግዚአብሔር ፡ ጽድቅን (እውነት) ፡ ሿት ፡ በእርሷም ፡ ፍረዱ ፡ ብሏል ። (ኢሳ ፡ ፩ ፡ ፲፯) ። የተጣሉ ፡ ሰዎች ፡ በፊታችሁ ፡ ሲከራከሩ ፡ ለፍርድ ፡ በተቀመጣችሁ ፡ ጊዜ ፡ እስኪታረቁ ፡ ድረስ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ወንድሞች፡ አትበሏቸው ። ዕዳቸውንም ፡ በእውነት ፡ ይቅር በሏቸው ።

፩ሺ.፩፻፹፯ ወናሁ ፡ ንቤ ፡ ከመ ፡ ኢይደሉ ፡ ትፍትሑ ፡ ላዕለ ፡ ፩ዱ ፡ ዘእንበለ ፡ ይብጽሑ ፡ ፪ኢሆሙ ፡ ኅቡረ ፡ እስመ ፡ አንትሙ ፡ ለእመ ፡ ሰማዕክሙ ፡ ቃለ ፡ ፩ዱ ፡ ወቅሰተ ፡ ዘእሁ ፡ ወፈታሕክሙ ፡ ፍጡነ ፡ እንዘ ፡ ኢሀለወ ፡ ካልኡ ፡ ምስሌክሙ ፡ ከመ ፡ ያውሥእ ፡ በእንተ ፡ ነፍሱ ፡ ትከውኑ ፡ አንትሙ ፡ ድልዋነ ፡ ለኰነኔ ፡ ዘፈታሕክሙ ፡ ቦቱ ፡ ወትከውኑ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አኃዜ ፡ ኰሉ ፡ ሱቱፋኒሁ ፡ ለሐሰት ፡ ወመከፈልተ ፡ ዚአሁ ።

፩ሺ.፩፻፹፯ አነሆ ፡ ሁለቱም ፡ በአንድነት ፡ ሳይቀርቡ ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ ልትፈርዱ ፡ እንዳይገባ ፡ ተናገርን ። ሌላው ፡ ስለራሱ ፡ መልስ ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ ሳይኖር ፡ የአንዱን ፡ ቃልና ፡ ክርክሩን ፡ ሰምታችሁ ፡ ፈጥናችሁ ፡ ብትፈርዱ ፡ በፈረዳችሁበት ፡ ፍርድ ፡ ለመቀጣት ፡ እናንተ ፡ ዝግጁዎች ፡ ትሆናላችሁና ። ሁሉን ፡ በያዘ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የሐሰት ፡ ተባባሪዎችና፡ የእርሷ ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ ትሆናላችሁ ።

፩ሺ.፩፻፹፰ መከ ፡ ጽወዐቱ ፡ ኢይደልዎ ፡ ለብእሲ ፡ ከመ፡ ይረሲ ፡ ገብረ ፡ ህየንቴሁ ፡ በእንተ ፡ ተዋቅሶ ፡ ቅሰት ፡ በኀበ ፡ ፈታሒ ፡ እስመ ፡ ኢይትዔረይ ፡ በክብረ ፡ ምስለ ፡ እግእዚ ፡ ገብር ።

፩ሺ.፩፻፹፰ መክ ፡ ጽ፯ ። ለሰው ፡ በዳኛ ፡ ዘንድ ፡ ስለጠቡ ክርክር ፡ ባሪያውን ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ሊያደርግ ፡ አይገባውም ። ባሪያ ፡ በክብር ፡ ከጌታው ፡ ጋር ፡ አይተካከልምና ።

፩ሺ.፩፻፹፱ ክፍል ፡ ፩ዱ ፡ ወአእምሮ ፡ ከመ ፡ አምጽኦ ፡ ስማዕት ፡ ለጥያቄ ፡ ላዕለ ፡ ዘይሰኪ ፡ ወመሐላሰ ላዕለ ፡ ዘይክሕድ ። ወለእመ ተሣመሩ በመ[illegible] ፡ ላዕለ ፡ ዘይሰኪ ፡ ዝኒ ፡ ይከውን ፡ ወይኅብአ ፡ ዕዳ ፡ ላዕለ ፡ ዘክሕደ ፡ ኪያሁ ፡ እስመ ፡ ሰካዪ ፡ ለሊሁ ፡ ኅሣሢሁ ፡ ውእቱ ፡ ወዘይሰክዮ ዎሂ ፡ ለሊሁ ዘይትኀሠሥ እምኔሁ ። ወሰከየ ትሰ ኢይከውን ፡ ዘእንበለ በዘውእቱ ብዉሕ ፡ ላዕለ ፡ አስተዋፅኦቱ ፡ ለዘይሰኪ ፡ በእንቲአሁ ፡ በከመ ፡ ብዉሕ ፡ ላዕለ ፡ አስተዋፅኦቱ ፡ ውእቱ ፡ ዘይሰክዮዎ ፡ ቦቱ ፡ በእንቲአሁ ።

፩ሺ.፩፻፹፱ ክፍል ፡ ፩ ። የማስረጃ ፡ ምስክር ፡ ማምጣት ፡ ለከሳሽ ፡ እንደሆነ ፡ አወቅ ። መሐላ ፡ ግን ፡ ለሚክድ ፡ ነው ፡ በከሳሽ ፡ ላይ ፡ በመሐላው ፡ ቢስማሙ ፡ ይህም ፡ ይሆናል ። ዕዳም ፡ እርሱን ፡ ወደ፡ ካደ ፡ ይመለሳል ። ከሳሽ ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ ፈላጊው ፡ ነውና ፡ ተከሳሽ ፡ ግን ፡ ከእርሱ ፡ የሚፈለግበት ፡ ነውና ። ስለእርሱ ፡ የከሰሱትም ፡ ሰው፡ በማወጣጣቱ ፡ ላይ ፡ እንደሚገባው ፡ ክስ ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ የተከሰሰበትን ፡ ለማወጣጣት ፡ ሥልጣን ፡ ባለው ፡ ላይ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አይሆንም ።

፩ሺ.፩፻፺ ወእምከመ ፡ በጽሑ ፡ ፪ኤሆሙ ፡ ተጻላእያን ለተፋትሖ ፡ ይበልዎሙ ፈታሒ በሉ ተናገሩ ፡ ወለሊሁኒ ያርምም እስከ ይትናገሩ ። ወለእመ ፡ ሰከዩ ፡ ለለ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ይቅድም ዘሰከየ አቅዲሙ ፡ ወእምከመ ፈጸመ ነገረ ቅሰቱ ፡ ይስምዑ ቅሰተ ካልኡ ። ወለእመ ኀሰ ፩ዱ በነገር ለካልኡ ፡ አው

፩ሺ.፩፻፺ ሁለቱ ፡ ተከራካሪዎች ፡ ለመፋረድ ፡ ከቀረቡ ፡ ዳኛው ፡ በሉ ፡ ተናገሩ ፡ ይበላቸው ። እርሱም ፡ እስኪናገሩ ፡ ድረስ ፡ ዝም ፡ ይበል ። ከእነርሱም ፡ አያንዳንዱ ፡ ቢካሰሱ ፡ አስቀድሞ ፡ የከሰሰው ፡ ይቅደም ። (ከሳሽ) ፡ የጠቡን ፡ ነገር ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ የሌላውን ፡ (የተካሳሽን) ፡ ክርክር ፡ ይስሙ ። አንዱ ፡ ሌላውን ፡ በነገር ፡ ቢነካው ፡

አንቀጽ ፡ ፵፫ ።

አውፅአ ፡ ቃለ ፡ ሕሡመ ፡ ይክልኦ ፡ ወለእመ ደገመ ፡ ይገሥጽ ፡ ወእመኒ ፡ ወሰከ ፡ ያውግዞ ።

፩ሺ.፬፻፸፩ ወዘሂ ፡ ሰከየ ፡ ግብረ ፡ ዘኢይትሌበው ይበሎ ፡ አጠይቅ ፡ ነገረከ ፡ ዘሰከይከ ፡ በእንቲ አሁ ። ወኢይፍታሕ ፡ በዘሰከየ ፡ እስከ ፡ ያዜ ክር ፡ ንዋየ ፡ ዘእሙር ፡ ከዋኒሁ ፡ ለንባብ ፡ ዘኢ ይትዌለጥ ፡ ከመ ፡ ዘይብል ፡ አነ ፡ ወሀብክዎ ፡ ፻ ፡ ዲናራተ ፡ ዘምስር ፡ ወበእንተ ፡ ዘኮነ ፡ ዲና ራት ፡ ዘምስር ፡ ከዋኒሁ ፡ ውእቱ ፡ ዝንቱ ፡ ወበ እንተ ፡ ዘኮነት ፡ ኍላቌሃ ፡ ፻ ፡ ውእቱ ፡ ወለእ መኒ ፡ ሰከየ ፡ ሰከየተ ፡ ዘጥዩቅ ፡ ወዘይትሌቦ ይበሎ ፡ ለካልኡ ፡ ምንተ ፡ ትብል ፡ ወለእመኒ ፡ አምነ ፡ ወእምዝ ፡ ይበሎ ፡ ለሰካዪ ፡ ናሁ ፡ ተአመነ ፡ ለከ ፡ ወለእመ ፡ ነሥሠ ፡ ንዋዮ ፡ ይፍ ታሕ ፡ ሎቱ ፡ በእንቲአሁ ፡ ላዕለ ፡ በዓለ ፡ ዕዳ ። ወእመኒ ፡ ክሕዶ ፡ ለዘሰከየ ፡ ኪያሁ ፡ ይበሎ ፡ ለዘክሕደ ፡ ብከኑ ፡ ሰምዕ ፡ ወለእመ ፡ ይቤ ፡ አልቦ ፡ ይበሎ ፡ ሰካዪ ፡ ትምሕለኑ ፡ ወእመኒ ፡ ፈርሀ ፡ መሐላ ፡ ወአግብአ ፡ ለዘሰከየ ፡ ወእ መኒ ፡ መሐለ ፡ ዘሰከየ ፡ ደለዎ ፡ ነሢአ ፡ ንዋዩ ። ወእመሰ ፡ ይቤ ፡ ካልኡ ፡ እምድኅረ ፡ ፈርሀ ፡ መሐላ ፡ አነ ፡ እምሕል ፡ ኢይሰምዖ ፡ እምኔሁ ፡ ዘእንበለ ፡ በሥምረተ ፡ ካልኡ ፤ አው ፡ ገብአ ፡ ውስተ ፡ ካልእ ፡ ዓውደ ፡ ምኩናን ፡ ወኢ አበየ ፡ ተመይጦ ፡ እመሐላ ፡ ኢይትከላእ ።

፩ሺ.፬፻፸፪ ወዘኒ ፡ ይቤ ፡ ብየ ፡ ጥያቄ ፡ ሰማዕት ፡ ከሡተ ፡ ወኅሡሥ ፡ መሐላ ፡ ዕድው ፡ እምበዓለ ፡ ዕዳሁ ፡ እምቅድመ ፡ ያብጽሕ ፡ ኪያሁ ፡ ኢያምሕሎ ፡ ሎቱ ፡ ወለእመ ፡ ይቤ ፡ ሰካዪ ፡ ብየ ፡ ጥያቄ ፡ ሰማዕት ፡ ወለእመ ፡ ይቤ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ እምድኅረ ፡ አበየ ፡ ይስምዕዎ ። ወለእመ ፡ ኮኑ ሰማዕታቲሁ ፡ ኢአካልያነ ፡ ይትኅሠሥዎ ፡ ከመ ፡ ይወስክ ፡ ለአጠይቆ ። ወለእመ ፡ ኮኑ ራትዓነ ፡ ወፍርሃት ፡ ውስቴቶሙ ፡ ይደልዎ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይፍልጥ ፡ ማእከሌሆሙ ፡ ወይ ሕትቶሙ ፡ ለለ፩ዱ ፡ ለኵሉ ፡ በእንተ ፡ ከዊነ ስምዕ ፡ ወጥያቄሃ ፡ ወመካና ፡ በከመ ፡ ገብረ ዳንኤል ፡ በጀቱ ፡ ረበናት ፡ እለ ፡ ኮኑ ፡ ሰምዐ ላዕለ ፡ ሶስና ። ወለእመ ፡ ኀብሩ ፡ ይገሥጽሙ በባሕቲቶሙ ፡ በአፍርሆ ፡ ወበተግዝሮ ፡ እም ግብራት ፡ ኀላፍያት ፡ ወኢኀላፍያት ፡ ወሰ ለተ ፡ ዕድሜ ፡ ወእዘክሮ ፡ በዘኮነ ፡ ቀዲሙ እምተግሣጽ ፡ እምላካዊ ፡ ላዕለ ፡ እለ ፡ ኮኑ ሰምዐ ፡ በሐሰት ፡ ወእምነ ፡ እማርያት ፡ መንፈ ሳውያት ፡ እስመ ፡ ገቢአ ፡ ኀበ ፡ ርትዕ ፡ ይኄ

ስለ ፡ ዳኛ ።

ወይም ፡ ከፉ ፡ ቃል ፡ ቢናገር ፡ ይከለክለው ። ቢደግምም ፡ ይቅጣው ። ቢጨምርም ፡ ይለየው።

፩ሺ.፬፻፸፩ በማይታወቅ ፡ ሥራ ፡ የከሰሰውንም ፡ ስለእ ርሱ ፡ የከሰሰበትን ፡ ነገር ፡ አስረዳ ፡ ይበለው ። የታወቀ ፡ የገንዘቡን ፡ አኳኋን ፡ በማይለወጥ ፡ አነጋገር ፡ እስኪያስረዳ ፡ ድረስ ፡ በክሳሽ ፡ አይ ፍረድበት ። እኔ ፡ እምሳ ፡ የምስር ፡ ዲናር ፡ ሰጠ ሁት ፡ እንደሚል ፡ ነው ። የምስር ፡ ዲናር ፡ ሁኔ ታዋ ፡ ይህ ፡ ስለሆነ ፡ ቍጥሯም ፡ ፶ ፡ ስለ ሆነ ፡ ነው ። የታወቀ ፡ የተረዳ ፡ ክስ ፡ ቢከስ ፡ ግን ፡ ተከሳሽን ፡ ምን ፡ ትላለህ ? ይበለው ። ቢያ ምን ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከሳሽን ፡ እነሆ ፡ አምኖል ሃል ፡ ይበለው ። ገንዘቡን ፡ ቢፈልግ ፡ ስለርሱ ፡ በባለ ፡ ዕዳው ፡ ላይ ፡ ይፍረድለት ። የከሰሰውን ፡ ቢክደው ፡ የካደውን ፡ ምስክር ፡ አለህን ? ይበ ለው ። የለኝም ፡ ቢል ፡ ከሳሽ ፡ ትምላለህን ? ይበለው ። መሐላውን ፡ ፈርቶ ፡ ለከሳሽ ፡ ቢመ ልስ ፡ (አንተ ፡ ማል ፡ ቢለው) ፡ ከሳሽም ፡ ቢም ል ፡ ገንዘቡን ፡ መቀበል ፡ ተገባው ። ተከሳሽ ፡ መሐላውን ፡ ከፈራ ፡ በኋላ ፡ እኔ ፡ እምላለሁ ፡ ቢል ፡ በከሳሽ ፡ ፈቃድ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አይ ሰሙት ። ወይም ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ የፍርድ ፡ ሸንጎ ፡ ቢመለስ ፡ (ይግባኝ ፡ ቢል) ፡ ከመሐላም ፡ መመ ለስን ፡ እንቢ ፡ ባይል ፡ አይከልከል ።

፩ሺ.፬፻፸፪ የታወቀ ፡ የምስክር ፡ ማስረጃ ፡ አለኝ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ባላጋራው ፡ ከባለዕዳው ፡ መሐላን ፡ ቢፈ ልግ ፡ እርሱን ፡ ሳያቀርብ ፡ አያምሉለት ። ከሳሽ፡ የምስክር ፡ ማስረጃ ፡ አለኝ ፡ ቢል ፡ ከእነርሱም ፡ አንዱ ፡ እንቢ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ አለብኝ ፡ ቢል ፡ ይሰሙት ። ምስክሮቹ ፡ የማይበቁ ፡ ቢሆኑ ፡ ለማረጋገጥ ፡ እንዲጨምር ፡ ይጠይቁት ። ቅኖ ች ፡ ቢሆኑ ፡ ፍርሃትም ፡ ቢኖራቸው ፡ በመካከላ ቸው ፡ ለይቶ ፡ እያንዳንዳቸውን ፡ ስለሚመሰክሩ በት ፡ ሁኔታ ፡ ስለማስረጃውና ፡ ስለቦታዋ ፡ ሊመረምራቸው ፡ ይገባዋል ። ዳንኤል ፡ በሶስና ፡ ላይ ፡ ምስክር ፡ በሆኑ ፡ በሁለቱ ፡ ረበናት ፡ እን ዳደረገ ። ቢተባበሩ ፡ ካለፉትና ፡ ካላለፉት ፡ ሥራ ዎች ፡ ከሰለተ ፡ ሞትም ፡ የተነሣ ፡ በማስፈራራ ትና ፡ በማስገረም ፡ ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ በሐ ሰት ፡ ምስክር ፡ በሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ከአምላ ካዊ ፡ ቅጣትና ፡ ከመንፈሳውያት ፡ ምልክቶች ፡ የተነሣ ፡ በማሳሰብ ፡ ይቅጣቸው ። ከንቱ ፡ ነገ ርን ፡ በመሥራት ፡ ከመደፋፈር ፡ ወደቅንነት ፡

ዖሰ ፡ እምቲኃብሎ ፡ ላዕለ ፡ ገቢረ ፡ ከንቱ ፡ እስመ ፡ እምገቢረ ፡ ከንቱ ፡ ንስሐ ፡ እምኔሁ ። ወአዝልፎሰ ፡ ላዕለ ፡ ገቢረ ፡ ከንቱ ፡ ወስከ ፡ ኃጢአት ፡ በዲበ ፡ ኃጢአት ።

፩ሺ፬፻፸፫ ወእመ ፡ ጸንዑ ፡ እምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ላዕለ ፡ ስምዐ ፡ ከዊን ፡ ወፍርሀት ፡ ሀሎ ፡ ውስቴቶሙ ፡ ይደልዎ ፡ ለቱ ፡ ከመ ፡ ይበሎ ፡ ለዘሰከዮ ፡ ንዋ ፡ ኮኑ ፡ ስምዐ ፡ ላዕሌከ ፡ እገሌ ፡ ወእገሌ ፡ ወተወከፍኩ ፡ ስምዖሙ ፡ ወንዋ ፡ አባሕኩከ ፡ እምተናቅፎ ፡ ሰማዕት ፡ ከመ ፡ ይፍታሕ ፡ ማእከሌሆሙ ፡ በአጠይቆ ፡ ሰማዕት ። ወለእመ ፡ ተነፍቀ ፡ ሰማዕታት ፡ በጥያቄ ፡ እመኒ ፡ ሆሎሙ ፡ አው ፡ ተርፈ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ትብጥል ፡ ሰማዕት ፡ ቀዳሚት ፡ እንተ ፡ እምጽአት ፡ ዕዳ ፡ በዘሰከዮ ፡ ቦቱ ፡ ወናሁ ፡ ተፈልጠ ፡ ፩ዱ ፡ እምአለ ፡ ያከውኑ ፡ ስምዐ ።

፩ሺ፬፻፸፬ ክፍል ፡ ፪ቱ ፡ ወእመኒ ፡ አርመመ ፡ ዘሰከይዎ ፡ ወኢአምነ ፡ ወኢክሕደ ፡ ይበሎ ፡ ፈታሒ ፡ ዳግመ ፡ በኀጊሁ ፡ ተሠጥዎ ፡ አውሥእ ፡ ወእመ ፡ አኮሰ ፡ ይደልወከ ፡ ቃለ ፡ መሐላ ፡ አው ፡ ተሐባዬ ፡ ሀብ ፡ በዘሰከዩከ ። ወለእመ ፡ ይቤ ፡ ዘሰከዮ ፡ ብየ ፡ ሰማዕት ፡ ከመ ፡ አልቦቱ ፡ ምንትኒ ፡ እምኀቤየ ፡ በዘይሰከየኒ ፡ የሀብዎ ፡ መዋዕለ ፡ ዕድሜ ፡ ለአብጽሖቶ ፡ ጥያቄሁ ፡ ወሰከዩኒ ፡ ይኅድግ ፡ እስከ ፡ ያመጽእ ፡ ሰማዕተ ። ወለእመ ፡ ተድኅረ ፡ እምነ ፡ ዕድሜ ፡ ዘዖደሉ ፡ ለአብጽሖቶ ፡ ጥያቄሁ ፡ ይደልዎ ፡ እመሂ ፡ መሐላ ፡ አው ፡ አሚን ። ወለእመኒ ፡ ኮነ ፡ ብዙኀ ፡ ንገር ፡ ማእከሌሆሙ ፡ ለሰማዕት ፡ ይፍታሕ ፡ ለዘጥዐ ፡ እምኔሆሙ ። ወለእመ ፡ ኢኀየለ ፡ ቃለ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ይፍትሑ ፡ በሀልዎቶሙ ፡ በከመ ፡ ይፈትሑ ፡ በኢሀልዎቶሙ ። ወቃልኒ ፡ ቃሉ ፡ ለዘሀሎ ፡ ንዋዩ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ ምስለ ፡ መሐላሁ ፡ ለእመ ፡ ኢያምጽአ ፡ ሰማዕተ ፡ ላዕለ ፡ ካልኡ ፡ በእንተ ፡ ፀሊዖቱ ።

፩ሺ፬፻፸፭ ወዘአሰተዋደየ ፡ ወዘተዐደወ ፡ ላዕለ ፡ ብእሲት ፡ እንተ ፡ ኢለመደት ፡ ተፋትሖ ፡ ወኢሐዊረ ፡ ፍኖት ፡ ኀበ ፡ ተጋይኦ ፡ ወተናግሮ ፡ ኢየገብርዋ ፡ ለበጺሕ ፡ አላ ፡ ተአዝዝ ፡ ከመ ፡ ትሚጥ ፡ ላቲ ፡ ዘየንቲሃ ፡ ዘይቀውም ፡ በምትክማ ። ወእምከመ ፡ ደለወ ፡ ላዕሌሃ ፡ መሐላ ፡ ይፈኑ ፡ ኀቤሃ ፡ ዘያምሕላ ፡ ፩ደ ፡ እምፈታዊን ።

፩ሺ፬፻፸፮ ወይደልዎ ፡ ለፈታሒ ፡ ከመ ፡ ይጽሐፍ ፡

መመለስ ፡ ይሻላልና ። ከንቱ ፡ ነገርን ፡ ከመሥራት ፡ መመለስ ፡ ንስሐ ፡ ነውና ። ከንቱ ፡ ነገርን ፡ በመሥራት ፡ ማዘውተር ፡ ግን ፡ በኃጢአት ፡ ላይ ፡ ኃጢአት ፡ መጨመር ፡ ነው ።

፩ሺ፬፻፸፫ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ምስክር ፡ በመሆን ፡ ቢጸኑ ፡ ፍርሃትም ፡ ቢኖራቸው ፡ የከሰሱትን ፡ ሰው ፡ እገሌና ፡ እገሌ ፡ እነሆ ፡ ምስክር ፡ ሆነውብሃል ። ምስክርነታቸውንም ፡ ተቀብለሃል ። ምስክርነታቸውንም ፡ ለመንቀፍ ፡ ፈቅጄልሀ ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ በምስክሮች ፡ አስረጅነት ፡ በመካከላቸው ፡ ይፈርድ ፡ ዘንድ ፡ ይገባዋል ። ምስክሮችም ፡ በማስረዳት ፡ ጊዜ ፡ ቢለያዩ ፡ ሁሉም ፡ ወይም ፡ ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ ቢቀር ፡ በተከሳሹ ፡ ላይ ፡ ዕዳ ፡ ያመጣችበት ፡ የቀደመችቱ ፡ ምስክርነት ፡ ትፈርሳለች ። ምስክር ፡ ከሆኑት ፡ ሰዎች ፡ አንዱ ፡ እነሆ ፡ ተለይቷልና ።

፩ሺ፬፻፸፬ ክፍል ፡ ፪ ። የተከሰሰው ፡ ዝም ፡ ቢል ፡ ባያምን ፡ ወይም ፡ ባይክድ ፡ ዳግመኛም ፡ ዳኛው ፡ መልስ ፡ በመሻት ፡ መልስ ፡ ስጥ ፡ ያም ፡ ባይሆን ፡ የመሐላ ፡ ቃል ፡ ይገባሃል ፡ ወይም ፡ በከሰሱህ ፡ ነገር ፡ ዋስ ፡ ስጥ ፡ ይበለው ። የከሰሱት ፡ ሰው ፡ በከሰሰኝ ፡ ነገር ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ምንም ፡ እንደሌለው ፡ ምስክር ፡ አለኝ ፡ ቢል ፡ መረጃውን ፡ ለማቅረብ ፡ የቀጠሮ ፡ ቀን ፡ ይስጡት ። ከሳሹም ፡ ምስክሮቹን ፡ እስኪያመጣ ፡ ይተወው ። መረጃውን ፡ ለማቅረብ ፡ ከሚገባው ፡ ቀጠሮ ፡ ወደኋላ ፡ ቢል ፡ መሐላ ፡ ወይም ፡ ማመን ፡ ቢሆን ፡ ይገባዋል ። በምስክሮች ፡ መካከል ፡ የነገር ፡ ብዛት ፡ ቢሆን ፡ ከእነርሱ ፡ ላቸነፈው ፡ (ለበዛው) ፡ ይፍረዱ ። ከእነርሱ ፡ ያንዱ ፡ ቃል ፡ ባይበልጥ ፡ ባለመኖራቸው ፡ እንደሚፈርዱ ፡ በመኖራቸው ፡ ይፍረዱ ። ስለ መካዱም ፡ በተከሳሹ ፡ ላይ ፡ ምስክር ፡ ካላመጣ፡ ነገሩ ፡ ከመሐላው ፡ ጋራ ፡ በእጁ ፡ ገንዘብ ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ ነገር ፡ ነው ።

፩ሺ፬፻፸፭ መፋረድን ፡ ወደገበያ ፡ መንገድ ፡ መሄድን ፡ መነጋገርን ፡ ያለመደችውን ፡ ሴት ፡ ደፍሮ ፡ የከሰሰ ፡ ሰው ፡ ከዳኛ ፡ ድረሺ ፡ ብለው ፡ አያስገድዷት ። በመቋሚያዋ ፡ የሚተካ ፡ ነገረ ፡ ፈጅ ፡ ትሾም ፡ ዘንድ ፡ ትዘዝ ፡ እንጂ ፡ ለእርሷ ፡ መሐላ ፡ ከተገባትም ፡ የሚያምላት ፡ ከዳኞች ፡ ወገን ፡ አንዱን ፡ ወደ ፡ እርሷ ፡ ይላክ ።

፩ሺ፬፻፸፮ ለዳኛ ፡ በ፪ ፡ ወይም ፡ በማበዛ ፡ ምስክር ፡

አንቀጽ ፡ ፹፫ ።

ለተፋትሖ ፡ መጽሐፈ ፡ ዕውቀ ፡ ወፍሉጠ ፡ ነበ ፡ ካልእ ፡ ፈታሒ ፡ እንዘ ፡ ይከውን ፡ በውስቴቱ ፡ ስምዐ ፡ ላዕለ ፡ ነፍሱ ፡ በስምዐ ፡ ፪ቱ ፡ እው ፡ ዘይፈደፍድ ፡ ወለውእቱ ፡ ፈታሒ ፡ ካልእ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይነጽር ፡ ውስተ ፡ ጠይቆተ ፡ ፍትሑ ፡ ወእምዝ ፡ ይፍታሕ ፡ ቦቱ ፡ ሶበ ፡ ተወከፈ ፡ ስምዖሙ ፡ ለሰማዕታት ፡ ዘውስቴቱ ። ወፍጻሜ ፡ ምዕራፍ ፡ ላብዕ ፡ በእንተ ፡ ፍትሐት ፡ ናሁ ፡ ይነግር ፡ በበእንቀጹ ፡ ፍትሑ ፡ ዘከመ ፡ ጕልታት ፡ ወከዊነ ፡ ግዕዛን ፡ ወአንብሮ ፡ ማኅፀንት ፡ ወትውህስታት ፡ ወሤጥ ፡ ወተዓስቦ ፡ ወተዋርሶ ፡ ወጽሒፈ ፡ ትእዛዝ ፡ ወዘይመስሎ ፡ ለዝንቱ ።

ስለ ፡ ዳኛ ።

ራሱ ፡ በውስጡ ፡ ምስክር ፡ ሁኖ ፡ ስመፈራረድ፡ የታወቀና ፡ የተለየ ፡ መዝገብ ፡ ወደሌላ ፡ ዳኛ ፡ ሊጽፍ ፡ ይገባዋል ። ለዚያም ፡ ስሌላው ፡ ዳኛ ፡ የፍርዱን ፡ እርግጠኛነት ፡ ሊመለከት ፡ ይገባዋል ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ በውስጡ ፡ ያሉትን ፡ የምስክሮችን ፡ ምስክርነት ፡ በተቀበለ ፡ ጊዜ ፡ (ከተቀበለ ፡ በኋላ) ፡ ይፍረድበት ። የሰባተኛው ፡ ምዕራፍ ፡ መጨረሻ ፡ ስለፍርዶች ፡ እነሆ ፡ በየፍርዱ ፡ እንቀጽ ፡ ይናገራል ። ይኸውም ፡ እንደ ፡ ጉልቶች ፡ እንደ ፡ ነጻነት ፡ ሁኔታ ፡ እንደ ፡ እደራ ማስቀመጥ ፡ እንደ ፡ ትውስቶችና ፡ እንደዋጋ ፡ እንደኪራይና ፡ እንደውርስ ፡ ትእዛዝን ፡ እንደ መጻፍና ፡ ይህንም ፡ እንደሚመስለው ፡ ያለ ፡ ነው ።

፩ሺ.፬፻፸፯ ምዕራፍ ፡ ሳምን ፡ በእንተ ፡ ገቢረ ፡ ዕርቅ ። ገቢረ ፡ ዕርቅሰ ፡ እዙዝ ፡ ውእቱ ፡ በእንተ ፡ ዘይቤ ፡ እግዚእነ ፡ በወንጌል ፡ "ሑር ፡ ቅድመ ፡ ወተበረቅ ፡ ምስለ ፡ እኁከ ፡ ወእምዝ ፡ ገቢእከ ፡ አብእ ፡ መባእከ ። ወብሂሎቱኒ ፡ ካዕበ ፡ ብፁዓን ፡ ገብርያነ ፡ ሰላም ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ውሉደ ፡ እግዚእብሔር ፡ ይሰመዩ ። ወሐዋርያትኒ ፡ ይቤሉ ፡ ኢመፍትው ፡ ለእግብርተ ፡ ክርስቶስ ፡ ተጻልኦ ።

፩ሺ.፬፻፸፯ ስምንተኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ዕርቅ ፡ ስለማድረግ ፡ ይናገራል ። ዕርቅ ፡ ማድረግስ ፡ የታዘዘ ፡ ነው ። ጌታችን ፡ በወንጌል ፡ አስቀድመህ ፡ ሂድና ፡ ከወንድምህ ፡ ጋር ፡ ታረቅ ። ከዚያም ፡ ተመልሰህ ፡ መባህን ፡ ስጥ ፡ ስላለ ፡ ነው ። (ማቴ ፡ ፭ ፡ ፳፫ - ፳፬) ። ዳግመኛም ፡ ዕርቅን ፡ የሚያደርጉ ፡ ሰዎች ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ እነርሱ ፡ የእግዚእብሔር ፡ ልጆች ፡ ይባላሉና ፡ በማለቱ ፡ ነው ። (ማቴ ፡ ፭ ፡ ፱) ። ሐዋርያትም ፡ ለክርስቶስ ፡ አገልጋዮች ፡ መጣላት ፡ አይገባቸውም ፡ ብለዋል ።

፩ሺ.፬፻፸፰ ዘኤፌሶን ፡ ፫ቱ ፡ ወይኩን ፡ ዘይፀውሮ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔክሙ ፡ ለካልኡ ፡ ወኩኑ ፡ ዕቁባነ ፡ በዐቂበ ፡ ፍቅር ፡ መንፈሳዊት ፡ በማእሰረ ፡ ዕርቅ ። ዘ፬ቱ ፡ ወኢታዕርቡ ፡ ፀሐየ ፡ ዲበ ፡ መዓትክሙ፡ ወኢትሀብዎ ፡ ፍኖተ ፡ ለሰይጣን ፡ ለእስሕቶትክሙ ።

፩ሺ.፬፻፸፰ ኤፌሶን ፡ ፫ ። ከእናንተ ፡ አንዱ ፡ ሌላውን ፡ የሚሸከመው ፡ ይሁን ። በዕርቅ ፡ ማሠሪያነት ፡ መንፈሳዊት ፡ ፍቅርን ፡ በመጠበቅ ፡ የተጠበቃችሁ ፡ ሁኑ ። (ኤፌ ፡ ፬ ፡ ፩ - ፫) ። ፬ ። በቁጣችሁ ላይ ፡ ፀሐይን ፡ አታስገቡ ። ለይጣንም ፡ እንዲያስታችሁ ፡ ጐዳና ፡ አትስጡት ። (ኤፌ ፡ ፬ ፡ ፳፮ - ፳፯) ።

፩ሺ.፬፻፸፱ ድስቅ ፡ ፰ቱ ፡ ወተዐቀቡ ፡ ከመ ፡ ትግበሩ ፡ ሰላመ ፡ ማእከለ ፡ ተጻላእያን ፡ እምቅድመ ፡ ይፃእ ፡ ፍትሕ ፡ እምኤጲስቆጶስ ፡ ወተፋትሖስ ፡ ኢኮነ ፡ ሠናየ ፡ በምንትኒ ፡ ግሙራ ፡ እመፍቅዳተ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ እስመ ፡ እመንድቦተ ፡ ፩ዱ ፡ ለካልእ ፡ በምንትኒ ፡ እመፍቅዳተ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ እምግብረ ፡ ሰይጣን ፡ ውእቱ ፡ ወእመክራሁ ። ወያፍቅሮ ፡ ሰብእ ፡ ወይሥዐር ፡ ዘንተ ፡ በኵኵዓ ፡ ወለእመኒ ፡ ውእቱ ፡ የኀጕል፡ ኅዳጠ ፡ እምንዋይ ፡ ይኄይሰከ ፡ ከመ ፡ ትኅጕል ፡ ኅዳጠ ፡ እምንዋይከ ፡ ወትኅጕእ ፡ ለተ

፩ሺ.፬፻፸፱ ድስቅ ፡ ፰ ። ከኤጲስቆጶስ ፡ ፍርድ ፡ ሳይወጣ፡ በተጣሉ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ዕርቅ ፡ ከማድረግ፡ ተጠበቁ ። ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ፈቃድ ፡ የተነሣ ፡ በማንኛውም ፡ ነገር ፡ መካሰስ ፡ ከቶ ፡ መልካም ፡ አይደለም ። ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ፈቃድ ፡ የተነሣ ፡ በማንኛውም ፡ ነገር ፡ አንዱ ፡ ሌላውን ፡ ማስጨነቅ ፡ ከሰይጣን ፡ ሥራ ፡ ከፈተናው ፡ የተገኘ ፡ ነውና ። ሰው ፡ ፈጥኖ ፡ በችኮላ ፡ ይህን ፡ ይሻር ። እርሱ ፡ ከገንዘቡ ፡ ጥቂት ፡ ቢያጠፋ ፡ አንተም ፡ ከገንዘብህ ፡ ጥቂት ፡ ብታጠፋ ፡ ከሰውም ፡ ሁሉ፡ ጋር ፡ ወንድሜ ፡ ወንድሜ ፡ ለመባባል ፡ ብትቸ

አንቀጽ ፡ ፵፪ ።

አኀዎተ ፡ ዙሉ ፡ ሰብእ ፡ እኮ ፡ ለእኃዊከ ፡ ባሕቲቶሙ ፡ እላ ፡ ምስለ ፡ ዙሎሙ ፡ እሕዛብ ፡ እስመ ፡ አንተ ፡ ለእመ ፡ ኀጕልከ ፡ ዘዝንቱ ፡ ዓለም ፡ እኮ ፡ ዘተኀጕለ ፡ እም ፡ ዘእግዚአብሔር እምክመ ፡ ኮንከ ፡ ላእከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘተሐዩ ፡ በትእዛዘ ፡ ክርስቶስ ። ለእለ ፡ ተበእሱ ፡ እስተጋብእዎሙ ፤ በተፋቅሮ ፡ ወለመስተጻርራን ፡ እስተሳልምዎሙ ፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ ሰንእዋነ ፡ እስመ ፡ እግዚእነ ፡ ይቤ ፡ ብፁዓን ፡ ገባርያነ ፡ ሰላም ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ውሉደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሰመዩ ።

፩ሺ፬፻፹ ዘ፲ወ፪ቱ ፤ ወእለሰ ፡ ይገብሩ ፡ ጽልእ ፡ ወጸብእ ፡ ወተጋእዞ ፡ ወተፋትሖ ፡ ዐማፅያን ፡ እሙንቱ ፡ ወነኪራን ፡ እምእግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ ምሕረት ፡ ውእቱ ።

፩ሺ፬፻፹፩ ዘቆሮንቶስ ፡ ፮ቱ ፡ "ናሁ ፡ እኩንንክሙ ፡ ሥጋክሙ ፡ ቅድመ ፡ እመ ፡ ኮንክሙ ፡ ተጻላእያነ ፡ ወትትገአዙ ፡ በበይናቲክሙ ፡ ወለምንት ፡ ዘኢትትዔገሉ ፡ ወለምንት ፡ ዘኢትትገፍዑ ፡ እላ ፡ እንትሙሰ ፡ ተዓጋልያን ፡ ወገፋዕያን ፡ እኃዊክሙ ፡ ካዕበ ፡ ኢተእምሩኑ ፡ ከመ ፡ ዐማፅያን ፡ ኢይወርስዋ ፡ ለመንግሥተ ፡ እግዚአብሔር" ።

፩ሺ፬፻፹፪ ወእእምር ፡ ከመ ፡ ዕርቅ ፡ ዘበእንተ ፡ ንዋይ ፡ በፍኖተ ፡ እርዮት ፡ ወውሂቦት ፡ ለቢዝዎ ፡ መሐላ ፡ ወመቲረ ፡ ተጻልእ ፡ ወተፋትሖ ፡ በእንተ ፡ ፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኅፈር ፡ እምሰብእ ። ወውእቱ ፡ ይትከፈል ፡ ኀበ ፡ ፫ቱ ፡ እክፋል ፡ ተዓርቆ ፡ ዘምስለ ፡ ተእምኖ ፡ ወዕርቅ ፡ ዘምስለ ፡ ክሒድ ፡ ወዕርቅ ፡ ዘምስለ ፡ እርምሞ ፡ ወውእቱ ፡ ሶበ ፡ ኢየእምን ፡ በዘይስክዮዎ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወኢይክሕድዎ ።

፩ሺ፬፻፹፫ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዕርቅ ፡ በእንተ ፡ ንዋይ ፡ በውሂበ ፡ ንዋይ ፡ ይትፌጸም ፡ በእንቲአሁ ፡ ውሂበ ፡ ንዋይ ፡ በእንተ ፡ ንዋይ ። ወይኩን ፡ ዘከመ ፡ ይገብሩ ፡ በምሥያጥ ፡ ወተማይጦ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዕርቅ ፡ በእንተ ፡ ንዋይ ፡ ዘቦቱ ፡ በቍዔት ፡ ይኩን ፡ በከመ ፡ ተበሰበ ፡ ወኩሉ ፡ ድልው ፡ ውእቱ ፡ ለእመ ፡ ኢኮነ ፡ ውስቴቱ ፡ ርዴ ፡ በአምሳል ፡ ለእመ ፡ ይከውን ፡ ዕርቅ ፡ በእንተ ፡ ፳ ፡ ርክብት ፡ በጊዜሃ ፡ ወ፴ ፡ በዕድሜ ፡ እው ፡ በመስፈርት ፡ እው ፡ በእንተ ፡ ሥርናይ ፡ ብሉይ ፡

ስለ ፡ ዳኛ ።

ኩል ፡ ይሻልሃል ። ለወንድሞችህ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። ከአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡ ነው ፡ እንጂ ። በክርስቶስ ፡ ትእዛዝ ፡ የምትኖር ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገልጋይ ፡ ከሆንክ ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ገንዘብ ፡ ብታጣ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የሚገኘውን ፡ የምታጣ ፡ አይደለህምና ። የተጣሉትን ፡ ሰዎች ፡ በፍቅር ፡ አንድ ፡ አድርጋቸው ። የተጣሉትንም ፡ አስታርቋቸው ። የተስማሙ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ። ጌታችን ፡ ሰላምን ፡ የሚያደርጉ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ። እነርሱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ይባላሉና ፡ ብሏልና ። (ማቴ ፡ ፭ ፡ ፱) ።

፩ሺ፬፻፹ ፲፪ ። ጠብን ፡ መጣላትን ፡ ክርክርንና ፡ መፋረድን ፡ የሚያደርጉ ፡ ሰዎች ፡ ዓመፀኞች ፡ ናቸው ። ከእግዚአብሔርም ፡ የተለዩ ፡ ናቸው ። እግዚአብሔር ፡ የይቅርታ ፡ አምላክ ፡ ነውና ።

፩ሺ፬፻፹፩ ቆሮንቶስ ፡ ፮ ። እነሆ ፡ እርስበርሳችሁ ፡ የምትጣሉና ፡ የምትከራከሩ ፡ በነበራችሁበት ፡ ጊዜ ፡ ሥጋችሁን ፡ አስገዝታችሁ ፡ ነበረ ። የማትቀሙ ፡ ለምንድን ፡ ነው ? የማትበደሉስ ፡ ለምንድን ፡ ነው ? እናንተስ ፡ ገና ፡ ሁለተኛ ፡ ወንድሞቻችሁን፡የምትቀሙ፡የምትበድሉም፡ናችሁ። ዓመፀኞች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ እንዳይወርሱ ፡ እታውቁምን ? (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፯ - ፲፩) ።

፩ሺ፬፻፹፪ ስለታወቀ ፡ ገንዘብ ፡ የሚሆን ፡ ዕርቅ ፡ በማስተካከል ፡ መንገድ ፡ መሐላን ፡ ለመበዝበዝት ፡ (ለማስቀረት) ፤ ስለእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ከሰው ፡ ስለማፈር ፡ መፋረድንና ፡ መጣላትን ፡ ለመቁረጥ ፡ እንደሆነ ፡ እወቅ ። እርሱም ፡ ከ፫ ፡ ይከፈላል ። ከማንም ፡ ጋራ ፡ የሚሆን ፡ ዕርቅ ፡ ከመካድም ፡ ጋር ፡ የሚሆን ፡ ዕርቅ ፡ ከዝምታም ጋር ፡ የሚሆን ፡ ዕርቅ ፡ አለ ። ይኸውም ፡ በከሰሱት ፡ ነገር ፡ ባያምን ፡ ወይም ፡ ባይክድ ፡ ነው ።

፩ሺ፬፻፹፫ ስለገንዘብ ፡ የሚሆን ፡ ዕርቅ ፡ ገንዘብ ፡ በመስጠት ፡ ቢሆን ፡ ስለእርሱ ፡ የገንዘብ ፡ ስጦታ ፡ ስለገንዘብ ፡ ይፈጸማል ። በመሸጥና ፡ በመግዛት ፡ ጊዜ ፡ እንደሚያደርጉት ፡ ይሁን ። ዕርቁ ፡ ትርፍ ፡ ስላለው ፡ ገንዘብ ፡ ቢሆን ፡ እንደተዋዋሉት ፡ ይሁን ። አራጣ ፡ ከሌለበት ፡ ሁሉ ፡ የተገባ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ ዕርቁ ፡ በጊዜዋ ፡ በተገኘች ፡ በኻያ ፡ በቀጠሮ ፡ ፴ ፡ ወይም ፡ በመስፈሪያ ፡ ወይም ፡ ስለከረመ ፡ ስንዴና ፡ አዲስ ፡ ስንዴ ፡ በቀጠሮ ፡ ስለመስጠት ፡ ቢሆን ፡ በእ

ወሙሂበ ፡ ሥርናዩ ፡ ሐዲስ ፡ በዕድሜሁ ፡ ይደሉ ፡ አሙን ።

፩ሺ፬፻፹፬ ወይሙበር ፡ ዕርቅ ፡ በተሥዕሮ ፡ ትእዛዛቲሁ ፡ በአምሳል ፡ ዘይከውን ፡ ዕርቅ ፡ ላዕለ ፡ ፍዳ ፡ በጊዜ ፡ እሙር ፡ ወኢወሀበ ፡ በውእቱ ፡ ጊዜ ፡ አው ፡ በግብር ፡ እሙር ፡ ወየአቢ ፡ ከመ ፡ ኢይሥርዖ ፡ በቱ ፡ እምውእቱ ፡ መንፈቀ ፡ ወዕር ቅስ ፡ ላዕለ ፡ ዕዳ ፡ ዘእንበለ ፡ ግብሩ ፡ አው ፡ ዘእ ንበለ ፡ ጊዜሁ ፡ ዘከመ ፡ ውዕቡ ፡ ዕዳ ፡ ወዕርቅ ፡ ላዕለ ፡ ካልእ ፡ እምዕዳ ፡ በዘይመስሎ ፡ በጊዜሁ ፡ ኅደገ ፡ ሎቱ ፡ ዕዳ ፡ ካልእ ።

፩ሺ፬፻፹፬ በትእዛዙ ፡ መሻር ፡ ዕርቅ ፡ ይሻራል ። ለምሳሌ ፡ በታወቀ ፡ ጊዜ ፡ ስመክፈል ፡ የተ ደረገ ፡ ዕርቅ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ባይሰጥ ፡ ወይም ፡ በታወቀ ፡ ሥራ ፡ በእኩሌታው ፡ እንዳይ ሠሩበት ፡ እንቢ ፡ ቢል ፡ ያፈርሳል ። ያለ ፡ ሥራው ፡ ወይም ፡ ያለጊዜው ፡ በዕዳ ፡ የሚሆ ን ፡ ዕርቅስ ፡ ዕዳን ፡ እንደመሸጥ ፡ ያለ ፡ ነው ። ከዕዳ ፡ ወገን ፡ በሌላ ፡ ላይ ፡ የሚሆንም ፡ ዕርቅ ፡ በሚመስለው ፡ ሁናቴ ፡ በጊዜው ፡ ሌላውን ፡ ዕዳ ፡ ይተውለት ።

፩ሺ፬፻፹፭ ምስራፍ ፡ ፱ቱ ። በእንተ ፡ ከመ ፡ ኢይትፋ ትሑ ፡ ምእመናን ፡ በኀበ ፡ አለ ፡ ኢየአምኑ ፡ ወከመ ፡ ይኩኑ ፡ ፈታሕት ፡ እምሊቃን ፡ ካህ ናት ፡ አው ፡ እምካህናት ፡ ወከመ ፡ ኢይፍታሕ ፡ ፩ዱ ፡ ለርእሱ ፡ ወከመ ፡ ኢይእበዩ ፡ ፍዱሃ ፡ እምበጺሕ ፡ ኀበ ፡ ፈታሒ ፡ ሶበ ፡ ጸውዕዎ ፡ ለተ ፋትሖ ። ይቤ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ዘቆሮንቶስ፡ ፮ቱ ፡ "ለእመቦ ፡ ዘቦ ፡ ተስናን ፡ ምስለ ፡ ቢጹ ፡ ይትዋቀሱ ፡ በኀበ ፡ ቅዱሳን ፡ ወአኮ ፡ በኀበ ፡ ጸአልያን ፡ ወዐማፅያን ፡ አላ ፡ በኀበ ፡ ቅዱ ሳን ፡ ወንጹሓን ፡ ወኢተአምሩኑ ፡ ከመ ፡ ንጹ ሓን ፡ ይኴንንዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ዓለም ። ወለእመ ፡ ሰኪ ፡ ዓለም ፡ ትትኴነኑ ፡ ብከሙ ፡ ኢኮንክሙኑ ድልዋነ ፡ ከመ ፡ ትፍትሑ ፡ ዘንተ ፡ ፍትሐ ፡ ንኡሰ ፡ አው ፡ ኢተአምሩኑ ፡ ከመ ፡ ንሕነ ፡ ንኴ ንኖሙ ፡ ለመላእክት ፡ እፎኬ ፡ ዘኮነ ፡ ውስተ ፡ ዛቲ ፡ ዓለም" ። ወባሕቱ ፡ ለእመ ፡ ኮነት ፡ ማእ ከሌክሙ ፡ ወማእከለ ፡ ፩ዱ ፡ እምሰብእ ፡ ዛቲ ፡ ዓለም ፡ ተጋእዞ ፡ እንብርዎሙ ፡ ምስሌክሙ ፡ ለእለ ፡ ይትሐሰሉ ፡ እመንበሮ ፡ ሢመተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለሬእዎሙ ፡ ፍትሕ ፡ ማእከሌክሙ ። ወዘንተሰ ፡ ዘእቤ ፡ ከመ ፡ ትኀፈሩ ፡ ወከመዝኑ ፡ አልቦ ፡ እምውስቴትክሙ ፡ ጠቢብ ፡ ወኢ ፩ዱ ፡ ዘይክል ፡ ፈቲሐ ፡ ማእከለ ፡ እኁሁ ፡ ወእ ኁሁ ፡ አላ ፡ ይጸልእ ፡ እኁ ፡ ለእኁሁ ፡ አው ይትፋትሑ ፡ ካዕበ ፡ በኀበ ፡ አለ ፡ ኢየአምኑ ።

፩ሺ፬፻፹፭ ፱ነኛ ፡ ምዕራፍ ። አማኞች ፡ በማያምኑት ፡ ዘንድ ፡ እንዳይፋረረዱ ፡ ፈራጆችም ፡ ከሊቃን ፡ ካህናት ፡ ወይም ፡ ከካህናት ፡ ወገን ፡ እንዲሆኑ ፡ አንዱም ፡ ለራሱ ፡ እንዳይፈርድ ፡ አንድ ፡ ሰውስ፡ እንኳ ፡ ለፍርድ ፡ በጠሩት ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ዳኛ ፡ ከመድረስ ፡ እንቢ ፡ እንዳይል ፡ ይናገራል ። ሐዋ ርያ ፡ ጳውሎስ ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ቆሮ ፡ ፮ ። ከባል ንጀራው ፡ ጋር ፡ ጥል ያለው ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ በቅዱሳን ፡ ዘንድ ፡ ይከራከሩ ። በተሳዳቢዎችና፡ በዓመፀኞች ፡ ዘንድ ፡ አይደለም ። በቅዱሳንና ፡ በንጹሓን ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ። ንጹሓን ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ እንዲገዙት ፡ አታውቁምን ? ዓለምም ፡ በእናንተ ፡ የምትገዛ ፡ ከሆነች ፡ ይህን ትንሽ ፡ ፍርድ ፡ ልትፈርዱ ፡ ዘማዶዎች ፡ አልሆ ናችሁምን ? ወይስ ፡ እኛ ፡ መላእክትን ፡ እንድን ገዛቸው ፡ አታውቁምን ? በዚህች ፡ ዓለም ፡ የሆነ ውንማ ፡ እንደምን ፡ አንገዛ ? ነገር ግን ፡ በእና ንተና ፡ ከሰብእ ፡ ዓለም ፡ በአንዱ ፡ መካከል ፡ ክርክር ፡ ቢኖር ፡ በመካከላችሁ ፡ ፍርድን ፡ ለመ ፈጸም ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሹመት ፡ መዓርግ፡ ዝቅ ፡ ያሉትን ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ አስቀምጧ ቸው ። ይህንም ፡ ማለቴ ፡ ታፍሩ ፡ ዘንድ ፡ ነው። ወንድም ፡ ወንድሙን ፡ እስኪጣላው ፡ ወይም ፡ ዳግመኛ ፡ በኢአማንያን ፡ ዘንድ ፡ እስኪፋረደው ድረስ ፡ በወንድምና ፡ በወንድም ፡ መካከል ፡ መፍረድ ፡ የሚችል ፡ አንድ ፡ እንኳ ፡ ብልህ ፡ ከውስጣችሁ ፡ እንደዚህ ፡ የለምን ? (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፩ - ፮) ።

፩ሺ፬፻፹፮ ድስቅ ፡ ፳ቱ ፡ ኢይሑር ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ኀበ ፡ መሰፍን ፡ አሕዛብ ፡ ወኢኀበ ፡ ሊቃናተ ፡ ዐላ ውያን ፡ ከመ ፡ ይፍትሑ ፡ ሎቱ ፡ ወኢበምንትኒ፡

፩ሺ፬፻፹፮ ድስቅ ፡ ፳ ። ክርስቲያናዊ ፡ ከሥራዎች ፡ በማ ናቸውም ፡ ይፈርዱለት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ ገዥና ፡ ወደ ፡ አዐላውያን ፡ አለቆች ፡ አይሂድ ።

አንቀጽ ፡ ፵፫ ።

እምግብራት ፡ እስመ ፡ ሰይጣን ፡ ያስተዴሉ ፡ መሣግረ ፡ ብዙኃተ ፡ ለእግብርተ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ እመንገለ ፡ መንፈቆሙ ፡ በበይናቲሆሙ ። ወይከውኖሙ ፡ ነውረ ፡ ከመ ፡ ዘውእቶሙ ፡ እልቦ ፡ በውስቴቶሙ ፡ ጠቢብ ፡ ወኢ፩ዱ ፡ ዘይ ክል ፡ ከመ ፡ የሀሉ ፡ በማእከሌሆሙ ፡ ወዘየእ ምር ፡ ፍትሐ ፡ ኵሉ ፡ ለለ፩ዱ ፡ ወዘያድኅኖ ፡ እምካልኡ ፡ ከመ ፡ ይሰስል ፡ ሀከክ ፡ ወኢትን ድግዎሙ ፡ ዓዲ ፡ ለአሕዛብ ፡ ያእምሩ ፡ ምን ተኒ ፡ እምተኃእዞ ፡ ዘይከውን ፡ ማእከሌክሙ ።

ሰይጣን ፡ በእኩሌቶቹ ፡ በኩል ፡ እርስ ፡ በርሳ ቸው ፡ ለማጣላት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አገልጋ ዮች ፡ ብዙ ፡ ወጥመድን ፡ ያዘጋጃልና ። ከእነርሱ በውስጣቸው ፡ የእያንዳንዱን ፡ ሁሉ ፡ ፍርድ ፡ የሚያውቅና ፡ የሚችል ፡ ክርክርም ፡ ይርቅ ፡ ዘንድ ፡ ከሌላው ፡ የሚያድነው ፡ አንድስ ፡ እንኳ ፡ ብልሀ ፡ እንደሌለ ፡ አድርጎ ፡ ነውር ፡ ይሆንባቸዋል ። ዳግመኛም ፡ አሕዛብን ፡ እንዲ ቀመጡ ፡ አትተውዋቸው ፡ በመካከላችሁ ፡ የሚሆነውን ፡ ክርክር ፡ ምንም ፡ ምን ፡ እንዳያ ውቁ ።

፩ሺ.፬፻፹፯ በስ ፡ ፺ወ፪ቱ ፡ ወኵሉ ፡ ፍትሐት ፡ ዘካህናት ፡ ኢይሰድዎ ፡ ኀበ ፡ መኳንንት ፡ አላ ፡ ያምጽእዎ ፡ ኀበ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወኀበ ፡ ሊቆሙ ፡ ለቀሳው ስት ፡ ከመ ፡ ይፍትሑ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ወእኮ ፡ መኳንንት ፡ ውእቶሙ ፡ ዘይፈትሑ ፡ ላዕለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አላ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይእቲ እንተ ፡ ትፈትሕ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ለለ፩ዱ ።

፩ሺ.፬፻፹፯ በስ ፡ ፺፪ ። የካህናቱን ፡ ፍርድ ፡ ሁሉ ፡ ወደ መኳንንቱ ፡ አይውሰዱት ። ይፈርዱላቸው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤጲስቆጶስና ፡ ወደ ፡ ቀሳውስት ፡ አለቃ ፡ ያምጡት ፡ እንጂ ። መኳንንትም ፡ በቤ ተክርስቲያን ፡ የሚፈርዱ ፡ አይደሉም ። በእያን ዳንዱ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ የምትፈርድ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ናት ፡ እንጂ ።

፩ሺ.፬፻፹፰ መጅ ፡ ፲ወ፩ ፡ ወእመቦ ፡ ዘኮነ ፡ ማእከሌሁ ፡ ወማእከለ ፡ ፩ዱ ፡ ተኃእዞ ፡ ወኢመጽአ ፡ ኀበ ፡ ፈታሒ ፡ ወተፈልጠ ፡ በምክረ ፡ ነፍሱ ፡ እመ ንገለ ፡ ተሠልጦ ፡ ወተኃይሎ ፡ ለነሚእ ፡ እም በዓለ ፡ ዕዳሁ ፡ ኢየሀብዎ ፡ ሎቱ ፡ ምንተኒ ፡ እምንዋዩ ። ወለእመ ፡ ነሥአ ፡ ዘኢኮነ ፡ ዚአሁ ፡ ያቅርብዎ ፡ ኀበ ፡ ሊቀ ፡ መካን ፡ ዘሀለወ ፡ ቦቱ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ይገሥጾ ። ወለእመ ፡ ኢገ ብአ ፡ ኀበ ፡ ሊቅ ፡ ከመ ፡ ይፍታሕ ፡ ሎቱ ፡ ወረ ሰየ ፡ ርእሶ ፡ ሀየንተ ፡ ፈታሒ ፡ ዘይትቤቀል ፡ ወነ ሥአ ፡ ንዋዮ ፡ ዘእንበለ ፡ ፍትሕ ፡ መኰንን ፡ ያግብእ ፡ ዘነሥአ ፡ እምኔሁ ።

፩ሺ.፬፻፹፰ መጅ ፡ ፲፩ ። በእርሱና ፡ በአንዱ ፡ መካከል ፡ ክርክር ፡ ቢኖር ፡ ወደ ፡ ዳኛም ፡ ባይመጣ ፡ ከባ ለዕዳው ፡ ላይ ፡ የሚወሰደውን ፡ ገንዘብ ፡ በሥ ልጣኑና ፡ በኀይሉ ፡ ለመውሰድ ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ የተለየ ፡ ቢሆን ፡ ከገንዘቡ ፡ ለእርሱ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ አይስጡት ። የእርሱ ፡ ያልሆነው ንም ፡ ገንዘብ ፡ ቢወስድ ፡ ይቀጣው ፡ ዘንድ ፡ ወደአለበት ፡ ዳኛ ፡ ያቅርቡት ። ይፈርድለትም ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ዳኛ ፡ ባይቀርብ ፡ ራሱንም ፡ እንደ ሚፈርድ ፡ ዳኛ ፡ ቢያደርግ ፡ ያለዳኛም ፡ ፍርድ ፡ ገንዘቡን ፡ ቢወስድ ፡ የወሰደውን ፡ ከእርሱ ፡ ይመልሱት ።

፩ሺ.፬፻፹፱ ጠስ ፡ ፴ወ፱ቱ ፡ ወለእመ ፡ ነሥአ ፡ ፩ዱ ፡ ምንተኒ ፡ እምእደ ፡ ካልኡ ፡ ዘእንበለ ፡ ፍትሐ ፡ ፈታሒ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘሂደ ፡ እምእዴሁ ፡ ዘዚአሁ ፡ ውእቱ ፡ ይፃእ ፡ እምኔሁ ፡ ምልክናሁ ፡ ወእመሰ ፡ ኮነ ፡ ዘካልኡ ፡ ያግብእ ፡ ኪያሁ ፡ ምስለ ፡ መጠነ ፡ ሤጡ ፡ ወተውሳከ ፡ ዝንቱኒ ። እመቦ ፡ ዘሰከዮዎ ፡ ኀበ ፡ ፈታሒ ፡ ወአበየ ፡ በጺሐ ፡ ወስምዐ ፡ ኮኑ ፡ ላዕሌሁ ፡ እለ ፡ እሙን ፡ ቃሎሙ ፡ ይትገሠጽ ፡ እው ፡ ይትወነዝ ፡ እስከ ፡ ይበጽሕ ፡ ኀበ ፡ መንበረ ፡ ፍትሕ ፡ ለተፋትሖ ።

፩ሺ.፬፻፹፱ ጠስ ፡ ፴፱ ። አንድ ፡ ሰው ፡ ከሌላው ፡ እጅ ፡ ያለዳኛ ፡ ፍርድ ፡ አንዳች ፡ ቢወስድ ፡ ከእጁም ፡ የቀማው ፡ የእርሱ ፡ ገንዘብ ፡ ቢሆን ፡ ገንዘብ ነቱ ፡ ከእርሱ ፡ ይውጣ ። የሌላው ፡ ገንዘብ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ከዋጋው ፡ ልክና ፡ ካጠፈታው ፡ ጋር ፡ እርሱን ፡ (ያንኑ) ፡ ይመልስ ። በዳኛ ፡ የከ ሰሱት ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ መቅረብንም ፡ እንቢ ፡ ቢል ፡ ቃላቸውም ፡ የታመነ ፡ ሰዎች ፡ ምስክር ፡ ቢሆኑበት ፡ ለመፋረድ ፡ ወደ ፡ ሸንጎ ፡ እስኪቀ ርብ ፡ ድረስ ፡ ይቀጣ ፡ ወይም ፡ ይለይ ፡ (ይታሰር)

፩ሺ.፬፻፺ ምዕራፍ ፡ ፲ቱ ። በእንተ ፡ ትእዛዛተ ፡ እዝል ፎቱ ፡ ለፈታሒ ። ወዛቲኒ ፡ ትበቍዕ ፡ ለሥር

፩ሺ.፬፻፺ ምዕራፍ ፡ ፲ ። ዳኛ ፡ እዘውትሮ ፡ ማዘዝ ፡ እንዲ ገባው ፡ ይናገራል ። ይህችም ፡ ለሹመቱ ፡ ውሳኔ

አንቀጽ ፡ ፵፫ ።

ዓተ ፡ ውሳኔ ፡ ዘሢመቱ ፡ ወለፍትሐ ፡ ኵነኔ ፡ ዘመዓርጉ ፡ ወለዘይትነገር ፡ በውስተ ፡ መጽሐፈ ፡ መባሕቲ ፡ ወጽሒፈ ፡ ትእዛዙ ፡ ወውሳኔያተ ፡ ፍትሑ ፡ ወለዘተርፈሂ ፡ በውስተ ፡ አንቀጸ ፡ መጽሐፍ ፡ እምዘተነግረ ።

፩ሺ፬፻፺፩ ወእምር ፡ ከመ ፡ ኵሉ ፡ ዘኢከልአዎ ፡ በጥንቱ ፡ ሢመቱ ፡ ፍትሐ ፡ ኵነኔ ፡ እኮ ፡ ዘይከልእዎ ፡ እምእዝልፎተ ፡ ሀልዎ ፡ በቱ ፡ እስመ ፡ ሢመቱ ፡ ይከውን ፡ ውስቴቱ ፡ ሰላመ ፡ ፍጽምተ ፡ ወወፂእስ ፡ እምሢመቱ ፡ ይከውን ፡ ውስቴቱ ፡ ታሕጻጸ ፡ ፍጹመ ። በአምሳል ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ዕንባዜ ፡ ውስተ ፡ ልቡ ፡ ወለእመ ፡ ኮኑ ፡ ይሴፈወ ፡ ተፈውሶቶ ፡ ይጸንሕዎ ፡ ወለእመ ፡ ኮኑ ፡ ዘኢይሴፈወ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ በጊዜ ፡ እሙር ፡ እምተረፈ ፡ ጊዜያት ፡ ይፁርዎ ፡ ወእመ አኮሰ ፡ አልቦ ።

፩ሺ፬፻፺፪ ምዕራፍ ፡ ፲ወ፩ዱ ። በእንተ ፡ ዐእቱ ፡ እምሢመቱ ። ኢይደልዎ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይሥዐር ፡ ነፍሶ ፡ ዘእንበለ ፡ በሥምረተ ፡ ዘሤሞ ፡ ወኢብውሕ ፡ ለዘሤሞ ፡ ከመ ፡ ይሥዐሮ ፡ ዘእንበለ ፡ በግብር ፡ ግሁድ ። ወለእመ ፡ ሠዐርዎ ፡ እው ፡ ተሥዕረ ፡ ይደሉ ፡ አግህዶቶ ፡ ሥዕረቱ ፡ በከመ ፡ ይደለወ ፡ አግህዶቶ ፡ ሢመቱ ፡ ከመ ፡ ትትመተር ፡ ተፋትሖ ፡ በኀቤሁ ።

፩ሺ፬፻፺፫ ወለእመ ፡ ፈትሐ ፡ እምድኅረ ፡ ሥዕረቱ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ እምድኅረ ፡ አእመረ ፡ ሥዕረተ ፡ ዘዚአሁ ፡ ኢይቀውም ፡ ፍትሑ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ እምቅድመ ፡ አእምሮቱ ፡ ይቀውም ፡ ፍትሑ ። ወኢይሥዐርዎሙ ፡ ለሥዩማኒሁ ፡ እለ ፡ ይፈትሑ ፡ ፍትሐ ፡ እምታሕቴሁ ፡ እስከ ፡ ይሥዕሮሙ ፡ ዘይሠየም ፡ እምድኅሬሁ ፡ በግብር ፡ ግሁድ ። ወለእመ ፡ ይቤ ፡ እምድኅረ ፡ ተሥዕሮቱ ፡ እንሰ ፡ ፈታሒከ ፡ በዘከመዝ ፡ ኢየአክል ፡ ባሕቲቱ ፡ እስከ ፡ ይከውን ፡ ሰምዐ ፡ ምስሌሁ ፡ ካልእ ፡ ሰማዕት ፡ ዝንቱሂ ፡ ለእመ ፡ ኢአደሞ ፡ ለ፩ዱ ፡ እምተጻላእያን ፡ እው ፡ ለእመ ፡ ኢያዕረግዎ ፡ ኀበ ፡ ዐባይ ፡ መዓርግ ፡ ከመ ፡ ዘይከውን ፡ ቀሲስ ፡ ወይከውን ፡ በጊዜ ፡ ዐእቱ ፡ እምፍትሕ ፡ ኀበ ፡ ሢመተ ፡ ኤጲስቆጶስና ፡ እው ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ።

፩ሺ፬፻፺፬ ምዕራፍ ፡ ፲ወ፪ቱ ። በእንተ ፡ ሰማዕታት ። ወውእቱ ፡ ፲ቱ ፡ ክፍል ፡ ቀዳሚ ፡ በእንተ ፡ ዘይደሉ ፡ ለሢመቶሙ ፡ ወያእምር ፡ በእንቲአሁ ፡

ሰለ ፡ ዳኛ ።

ደንብና ፡ ለመዓርጉ ፡ የቅጣት ፡ ፍርድ ፡ በሥልጣኑ ፡ ደብዳቤ ፡ ለሚነገረውም ፤ ለማዘዣው ፡ ደብዳቤም ፡ ለፍርዱም ፡ ውሳኔዎች ፡ በመጽሐፉ ፡ አንቀጽ ፡ ከተነገረውም ፡ ለቀረው ፡ ትጠቅማለች ።

፩ሺ፬፻፺፩ በሹመቱ ፡ መጀመሪያ ፡ የቅጣት ፡ ፍርድን ፡ ያልከለከሉት ፡ ሰው ፡ በእርሱ ፡ መኖርን ፡ ከማዘውተር ፡ የሚከለክሉት ፡ እንዳይደለ ፡ እወቅ ። ሹመቱ ፡ ፍጹም ፡ ሰላም ፡ ይሆናልና ። ከሹመቱ፡ መውጣትም ፡ ፍጹም ፡ ጉድለት ፡ ቢገኝበት ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ በልቡ ፡ ተላላነት ፡ ቢኖር ፡ መዳኑንም ፡ ተስፋ ፡ የሚያደርጉ ፡ ቢሆኑ ፡ ይጠብቁት ፡ ተስፋ ፡ የማያደርጉ ፡ ቢሆኑ ፡ ግን ፡ በቀሩት ፡ ጊዜያት ፡ በታወቀ ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ ይታገሡት ። ያለዚያ ፡ ግን ፡ ይሻሩት ።

፩ሺ፬፻፺፪ ምዕራፍ ፡ ፲፩ ፡ ከሹመት ፡ ስለሚወጣበት ፡ ይናገራል ። በሿሚው ፡ ፈቃድ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ራሱን ፡ ራሱ ፡ ሊሽር ፡ አይገባውም ። ለተሾመውም ፡ ሰው ፡ በተገለጸ ፡ ሥራ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር፡ ሊሽረው ፡ አይገባውም ። ቢሽሩት ፡ ወይም ፡ ቢሻር ፡ ሹመቱን ፡ መግለጽ ፡ እንደተገባ ፡ መሻሩንም ፡ መግለጽ ፡ ይገባል ። በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ መፋረረድ ፡ እንድትቀር ።

፩ሺ፬፻፺፫ ከመሻሩ ፡ በኋላ ፡ ቢፈርድ ፡ መሻሩን ፡ ካወቀ ፡ በኋላ ፡ ቢሆንም ፡ ፍርዱ ፡ አይጸናም ። ከማወቁ ፡ በፊት ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ፍርዱ ፡ ይጸናል ። ከበታቹ ፡ ፍርድ ፡ የሚፈርዱ ፡ ሹማምቱን ፡ ከእርሱ ፡ በኋላ ፡ የሚሾመው ፡ ሰው ፡ በተገለጸ ፡ ሥራ ፡ እስኪሽራቸው ፡ ድረስ ፡ አይሻሯቸው ። ከተሻረ ፡ በኋላ ፡ እኔ ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ፈርጄ ፡ ነበረ ፡ ቢል ፡ ሌላ ፡ ምስክር ፡ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ እስኪመሰክር ፡ ድረስ ፡ ብቻውን ፡ አይበቃም ። ይህም ፡ ከተባሉት ፡ አንዱን ፡ ባይወደው ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ከፍተኛ ፡ መዓርግ ፡ ባያወጡት ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ቄስ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ከፍርድ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ኤጲስቆጶስነት ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሊቀ ፡ ጵጵስና ፡ ሹመት ፡ እንደሚተላለፍ ፡ ነው ።

፩ሺ፬፻፺፬ ምዕራፍ ፡ ፲፪ ፡ ስለምስክሮች ፡ ይናገራል ። ይኸውም ፡ ፲ ፡ ክፍል ፡ ነው ። መጀመሪያ ፡ ለሹመታቸው ፡ ስለሚገባው ፡ ይናገራል ። ስለእር

አንቀጽ ፡ ፵፫ ።

መጽሐፍ ፡ ወልብ ፤ እመጽሐፍሰ ፡ ይብል ፡ እግዚአብሔር ፡ እምአፈ ፡ ፪ቱ ፡ ሰማዕታት ፡ አው ፡ ፫ቱ ፡ ይቁም ፡ ኵሉ ፡ ነገር ። ወጳውሎስኒ ፡ ይቤ ፡ ጤት ፡ ፭ቱ ፡ ወኢትትወከፍ ፡ ውዴተ ፡ በእንተ ፡ ቀሲስ ፡ ዘእንበለ ፡ በስምዐ ፡ ፪ቱ ፡ ሰብእ ፡ አው ፡ ፫ቱ ።

፩ሺ፬፻፺፭ በስ ፡ ፹ወ፪ቱ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ኢትፍታሕ ፡ ላዕለ ፡ ፩ዱኒ ፡ ዘእንበለ ፡ በሰማዕት ። ወዘተነግረሂ ፡ በተረፈ ፡ እሉ ፡ አክፋል ፡ ይኤምር ፡ ኀበ ፡ ዘይደሉ ፡ ተሠይሞቶሙ ፡ እስመ ፡ ግዕዛት ፡ ርኩባውያት ፡ ኢይከውና ፡ ዘእንበለ ፡ እለ ፡ ይትረከቡ ፡ እምከዊነ ፡ ግዕዞሙ ፡ ወፍትሐቲሆሙ ። ወልብኒ ፡ ውእቱ ፡ ዝንቱ ፡ ሶበ ፡ ኮኑ ፡ መንፈቆሙ ፡ ለሰብእ ፡ ራትዓነ ፡ ሰማዕተ ፡ ወመንፈቆሙሰ ፡ ኢኮኑ ፡ ራትዓነ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ያቅሙ ራትዓነ ፡ ለከዊነ ፡ ስምዕ ፡ ጊዜ ፡ ተፋትሖ ፡ በኀበ ፈታሒ ፡ እለ ፡ እሙን ፡ ቃሎሙ ፡ በጊዜ ፡ ተፋትሖ ፡ በእንተ ፡ ጥያቄ ፡ ጽድቅ ፡ ውኂዳገ ፡ ነገር ፡ ክንቱ ።

፩ሺ፬፻፺፮ ወበእንተ ፡ ከመ ፡ ልቡና ፡ ይፈትሕ ፡ በከዊነ ፡ አቅሞተ ፡ ሰማዕት ፡ ወተጋብአ ፡ አሐተኔ ፡ በግብር ፡ መፍትው ፡ ሎሙ ፡ አቅሞተ ፡ ሰማዕታት፡ በጊዜ ፡ ተፋትሖ ፡ በሥርዓተ ፡ ሕግ ፡ አምላካዊት ፡ ወበኀበ ፡ ካልእኒሆሙ ፡ እስመ ፡ ሰማዕታት ፡ ያጸንዑ ፡ ሕገ ፡ ጥያቄ ፡ ወተወክፎ ፡ መሐላ ፡ ፈድፋደ ፡ ወየአክል ፡ ዝንቱ ።

፩ሺ፬፻፺፯ ዳግም ፡ ሥርዓተ ፡ ሁሳኔ ፡ ዘይደልዎሙ ። ይቤ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ በትርጓሜሁ ፡ ብሥራተ ፡ ማቴዎስ ፡ ወዛቲስ ፡ ቃል ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ርትዕ ፡ እመኒ ፡ ኮነት ፡ ዘትትገበር ፡ ውስተ ፡ እሐቲ ፡ እምትሩፋት ፡ ባሕቲታ ፡ ዘውእቱ ፡ ቃለ ፡ ጽድቅ ፡ ይእቲስ ፡ ፈድፋደ ፡ ኢትትገበር ፡ ዘእንበለ ፡ ዘኮነት ፡ ሎቱ ፡ ኵሉ ፡ ምግባረ ፡ ትሩፋት ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ ዜናዊ ፡ ወኮኑ ፡ ፪ኤሆሙ ፡ ጻድቃነ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ። ወአጠየቀ ፡ ዘንተ ፡ ቃለ ፡ ወይቤ ፡ በንኢዶቱ ፡ ኪያሆሙ ፡ ወየሐውሩ ፡ በኵሉ ፡ ትእዛዛቲሁ ፡ ወጽድቁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘእንበለ ፡ ነውር ።

ስለ ፡ ዳኛ ።

ርሱም ፡ መጽሐፍና ፡ ልብ ፡ ያስረዳል ። ከመጽሐፍ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ በሁለት ፡ ወይም ፡ በሦስት ፡ ምስክር ፡ አፍ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ይጽና ፡ ብሏል ። (ዘዳ ፡ ፲፱ ፡ ፲፭) ። ጳውሎስም ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ጤት ፡ ፭ ። በ፪ ፡ ወይም ፡ በ፫ ፡ ሰዎች ፡ ምስክርነት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በቄሱ ፡ ላይ ፡ ነገረ ፡ ሥራ ፡ አትቀበል ። (፩ጢሞ ፡ ፭ ፡ ፲፱) ።

፩ሺ፬፻፺፭ በስ ፡ ፹፪ ። ኤጲስቆጶስ ፡ ሆይ ፡ በምስክር ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በአንዱም ፡ ላይ ፡ አትፍረድ ። ከእነዚህ ፡ ክፍሎች ፡ በቀረው ፡ የተነገረውም ፡ ሹመት ፡ ወደሚገባቸው ፡ ሰዎች ፡ ያመለክታል። የተገኙ ፡ ጠባዮች ፡ ከጠባያቸውና ፡ ከፍርዳቸው ሁኔታ ፡ የተነሣ ፡ የሚገኙ ፡ ካልሆኑ ፡ በቀር ፡ ለሹመት ፡ አያበቁምና ። ከልቡና ፡ የተባለውም ይህ ፡ ነው ። ከሰዎች ፡ እኩሌቶች ፡ እውነተኞች፡ ምስክሮች ፡ ቢሆኑ ፡ እኩሌቶች ፡ ግን ፡ እውነቶች ፡ ባይሆኑ ፡ እውነትን ፡ ስለመረዳትና ፡ ከንቱን ፡ ነገር ፡ ስለመተው ፡ በመፋረድ ፡ ጊዜ ፡ ቃላቸው ፡ የታመነውን ፤ በዳኛ ፡ ዘንድ ፡ በመፋረድ ፡ ጊዜ ፡ እውነተኞችን ፡ ምስክር ፡ ለመሆን ፡ ሊያቆሙ ፡ ይገባል ።

፩ሺ፬፻፺፮ ምስክር ፡ ስለመጥራትና ፡ በአንድነት ፡ በግድ ስለመሰብሰብ ፡ ሁኔታ ፡ ልቡና ፡ ስለሚፈርደው፡ ይናገራል ። በመፋረድ ፡ ጊዜ ፡ በአምላካዊት ፡ ሕግ ፡ ሥርዓትና ፡ በሌሎችም ፡ ዘንድ ፡ ምስክር፡ መጥፋት ፡ ለእነርሱ ፡ እግባብ ፡ ነው ። ምስክሮች ፡ የማስረጃውን ፡ ሕግ ፡ (እርግጡን) ፡ ይልቁንም ፡ መሐላ ፡ መቀበልን ፡ (ማማልን) ፡ ያጸናሉና ፡ ይህም ፡ ይበቃል ።

፩ሺ፬፻፺፯ ሁለተኛ ፡ የሚገባቸው ፡ የውሳኔ ፡ ደንብ ፡ ነው ። ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ በማቴዎስ ፡ ወንጌል ፡ ትርጓሜው ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ቅን ፡ የሆነች ፡ ይህች ፡ ቃል ፡ ከትሩፋት ፡ ወገን ፡ በአንዲቱ ፡ ምንም ፡ ብቻዋን ፡ የምትሠራ ፡ ብትሆን፤ ይኸውም ፡ የእውነት ፡ ቃል ፡ ነው ። ይህችስ ፡ የትሩፋት ፡ ሥራ ፡ ለሆነችው ፡ ሁሉ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ፈጽሞ ፡ አትደረግም ። ሰባኪው ፡ (ሉቃስ) ፡ እንደተናገረ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ሁለቱም ፡ እውነተኞች ፡ ሆኑ ። እነርሱንም ፡ በማመስገኑ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝና ፡ ሕግ ፡ ሁሉ፡ ያለነውር ፡ ይኖራሉ ፡ ብሎ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ አስረዳ ። (ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፯) ።

እንቀጽ ፡ ፵፫ ።

፩ሺ.፬፻ ፺፰ ወይቤሉ ፡ ሐዋርያት ፡ ድስቅ ፡ ፲፥ ፡ ወእለሂ ፡ ይከውኑ ፡ ስምዐ ፡ ይኩኑ ፡ ንጹሐነ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢመዓትማነ ፡ ዘይትእመንዎሙ ቅዱሳነ ፡ መፍቀርያነ ፡ ቢጽ ፡ መሐርያነ ፡ ዘኢ. አኩያን ፡ ወኢ ፡ ስሱዓን ፡ እላ ፡ መሐርያነ ፡ ኄራነ ፡ ለዘከመ ፡ እሉ ፡ ይትወከፉ ፡ ስምዖሙ ፡ በእንተ ፡ ሥነ ፡ ሐረቶሙ ፡ ወጽድቀ ፡ ቃሎሙ ፡ ወሥነ ፡ ምግባሮሙ ። ወለእለሰ ፡ ኮነ ፡ ሐረቶሙ ፡ በካልእ ፡ እምዝንቱ ፡ ኢይትወከፉ ፡ ስምዖሙ ፡ ወለእመኒ ፡ ነበረ ፡ ቃሎሙ ።

፩ሺ.፬፻ ፺፱ ጠስ ፡ ፳ወ፯፥ ፡ ወእለሂ ፡ ስምዐ ፡ ይከውኑ ፡ ለይኩኑ ፡ እምነ ፡ ሰብእ ፡ ዘይትአመንዎሙ ፡ ዘኢኮኑ ፡ ነዳያነ ፡ አእምሮ ፡ ወኢፍጹማነ ፡ በዕበድ ፡ ወዘሂ ፡ የኀሥሥዎ ፡ እምነ ፡ ሰማዕታት ፡ ክብረ ፡ መዓርግ ፡ ወሃይማኖት ፡ ወልማደ ፡ ምግባራት ፡ እንተ ፡ ትትዌደስ ። ወአእምሮ ፡ ከመ ፡ ከዊነ ፡ ርትዕ ፡ በኀበ ፡ ጠቢባን ፡ ውእቱ ፡ ለዘተፈጸመት ፡ ነፍሱ ፡ ነባቢት ፡ በትምህርተ ፡ አእምሮ ፡ ትሩፋት ፡ ወበምግባረ ፡ ሠናያት ፡ ወመለከት ፡ ላዕለ ፡ ኀይለ ፡ መዓት ፡ ወፍትወታት ፡ ወረሰዮቶሙ ፡ ይትለአኩ ፡ ለግብር ፡ መንፈሳዊ ፡ ወእስተራመመት ፡ በእሐቲ ፡ እምኔሆን ፡ ሁከታ ፡ ለካልእት ፡ ኀበ ፡ ኀሢሠ ፡ ሥጋውያት ። ወአእምር ፡ ከመ ፡ ዘይትፈቀድ ፡ እምኀበ ፡ እለ ፡ ይከውኑ ፡ ስምዐ ፡ ቃለ ፡ ጽድቅ ፡ ውእቱ ። ወሶበ ፡ ኮነ ፡ ዝንቱ ፡ ኢይትፈጸም ፡ ዘእንበለ ፡ በአእምሮ ፡ ወተፀምዶ ፡ ትሩፋት ፡ ወተግኅሦ ፡ እምኑፋት ፡ ደለወ ፡ ሥርዓተ ፡ ውሳኔሁ ፡ ለዘኢ. ይትፌጸም ፡ ቃለ ፡ ጽድቁ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘቦቱ ፡ ቃለ ፡ ጽድቅ ።

፩ሺ.፭፻ ሣልስ ፡ በእንተ ፡ ግብራተ ፡ ክልአት ፡ ዘበድልወት ። ድስቅ ፡ ፲፥ ፡ ኢይኩን ፡ ስምዐ ፡ ዘእንበለ ፡ ምእመን ። ጠስ ፡ ፳ወ፯፥ ፡ ወኢ ፡ ዘየሐጽጽ ፡ መዋዕሊሁ ፡ እም፳ ፡ ዓመት ፡ ወኢ ፡ ዘሀሎ ፡ ታሕተ ፡ ምግብና ፡ ወኢ ፡ ጽሙም ፡ ወኢ ፡ በሃም ፡ እው ፡ መስተዓብድ ፡ እው ፡ ዘይዘሩ ፡ ንዋዮ ፡ ወኢ ፡ ነዳይ ፡ ወኢገብር ፡ ኢ ፡ ዘፈትሐ ፡ ላዕሌሁ ፡ በገቢረ ፡ ዝሙት ፡ ወኢ ፡ እምእለ ፡ ይኤዝዝዎሙ ፡ ወይገሥጽዎሙ ፡ ዘከመ ፡ ሐራ

ስለ ፡ ዳኛ ።

፩ሺ.፬፻ ፺፰ ሐዋርያትም ፡ እንዲህ ፡ አሉ ። ድስቅ ፡ ፲ ። ምስክር ፡ የሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ንጹሐን ፡ የማይቆጡም ፡ ቅዱሳንም ፡ ብለው ፡ የሚያምኗቸው ፤ ጓደኛንም ፡ የሚወዱ፤ ይቅር ፡ ባዮች ፤ ቸሮች ፡ እንጂ ፤ ክፉዎች ፤ ወይም ፡ ስስታሞች ፡ ያይደሉ ፡ ይቅር ፡ ባዮች ፡ ይሁኑ ። እንደ ፡ እነዚህ ፡ ያሉትን ፡ ስለ ፡ አካሄዳቸው መበጀትና ፡ ስለ ፡ ቃላቸው ፡ እውነተኛነት ፤ ስለ ፡ ምግባራቸውም ፡ መበጀት ፡ ምስክርነታቸውን ፡ ይቀበሉ ። አካሄዳቸው ፡ ከዚህ ፡ በሌላ ፡ የሆነውን ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ቃላቸው ፡ ቢተባበር፡ ምስክርነታቸውን ፡ አይቀበሉ ።

፩ሺ.፬፻ ፺፱ ጠስ ፡ ፳፯ ። ምስክር ፡ የሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ከሚያምኗቸው ፡ ሰዎች ፡ ወገን ፡ እውቀት ፡ ያነሣቸው ፡ ፈጽመውም ፡ ሰነፎች ፡ ያልሆኑ ፡ ይሁኑ። ከምስክሮቹም ፡ የሚሹት ፡ የመዓርግ ፡ ክብርና፡ ሃይማኖት ፤ የምትመሰገንም ፡ የምግባር ፡ ልማድ ፡ ነው ። በዐዋቂዎች ፡ ዘንድ ፡ እውነተኛ ፡ መሆን ፡ ነባቢት ፡ ነፍሱ ፡ ትሩፋትን ፡ ለማወቅ ፡ በመማር ፡ በበጎ ፡ ሥራም ፡ ፍጽምት፡ ለሆነችለት ፡ ሰው ፡ እንደሆነ ፡ እወቅ ። የቍጣን ኀይልና ፡ ፍትወትን ፡ ለአስገዛችለት ፡ ለመንፈስ ሥራ ፡ እንዲያገለግሉ ፡ ለአደረገቻቸው ፤ ሥጋውያት ፡ ነገሮችንም ፡ ወደመሻት ፡ የሌላይቱን ፡ መታወክ ፡ ከእነዚህ ፡ በአንዲቱ ፡ ፀጥ ፡ ለአደረገችላቸው ፡ ሰዎች ፡ እንደሆነ ፡ እወቅ ። ምስክር ከሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ የሚፈለገው ፡ የእውነት ፡ ቃል ፡ እንደሆነ ፡ እወቅ ። ይኸውም ፡ የእውነት ፡ ቃል ፡ ያለው ፡ ቢሆን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በአእምሮና ፡ ለትሩፋት ፡ በመጽመድ ፤ ከተናቁ ፡ ነገሮችም ፡ በመራቅ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ የማይፈጸም ፡ ከሆነ ፡ የቃሉ ፡ እውነተኛነት ፡ ለማይፈጸምለት ፡ ሰው ፡ የውሳኔው ፡ ሥርዓት ተገባ ።

፩ሺ.፭፻ ሦስተኛው ፡ በሚገባ ፡ ስለመከልከል ፡ ሥራዎች ፡ ይናገራል ። ድስቅ ፡ ፲ ። የታመነ ፡ ካልሆነ ፡ ምስክር ፡ አይሁን ። ጠስ ፡ ፳፯ ። ዘመኑ ፡ ከ፳ ፡ ዓመት ፡ ያላነሰ ፤ በመተዳደር ፡ ሥር ፡ ያለ ፡ ወይም ፡ ደንቆሮ ፡ ወይም ፡ ዲዳ ፡ ወይም ፡ ወፈፌ ፡ (የሚያብድ) ፡ ወይም ፡ ገንዘቡን ፡ የሚበትን ፡ ወይም ፡ ድኃ ፡ ወይም ፡ ባሪያ ፡ ወይም ፡ በዝሙት ፡ ሥራ ፡ የፈረዱበት ፡ ወይም ፡ ከሚያዝዟቸውና ፡ ከሚቀጡዋቸው ፡ ወገን ፡ እነዚህም

አንቀጽ ፡ ፵፫ ።

ዘመ ፡ ለሥዩማን ፡ እሙ ፡ እምእለ ፡ ይበውኡ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ክፍለ ፡ በእንተ ፡ እምውሳኔያተ ፡ ጽድቅ ፡ ወዘይትዌሰክ ፡ ላዕለ ፡ እሉ ፡ ከመ ፡ ይከልእዎ ፡ እምከዊነ ፡ ስምዕ ፡ ለዘሰዐቦ ፡ አበሳሁ ፡ ዘከመ ፡ ነሢአ ፡ ዕቅብት ፡ ወስካር ፡ ወልሙድ ፡ ላዕለ ፡ ንኢሳን ፡ ከመ ፡ ዘዐበይት ፡ እልሐዝል ፡ ወእልመትምር ፡ ወእበርጉላ ፡ ወሕብረ ፡ ሰራ ፡ ላዕለ ፡ ፍኖት ፡ ወዘይበልዕ ፡ በውስተ ፡ ምሥያጥ ፡ ወዘይትሜሰል ፡ በአርአያ ፡ ዘኢኮነ ፡ አርአያሁ ፡ ከመ ፡ ካህን ፡ ዘይትከደም ፡ አው ፡ ዘየለብስ ፡ አልባሰ ፡ ሐራ ።

ስለ ፡ ዳኛ ።

እንደሽማምት ፡ ጭፍሮች ፡ ያሉ ፡ ናቸው ። ወይም ፡ ከእውነት ፡ ውሳኔ ፡ ወደዚህ ፡ የመውጣት ፡ ክፍል ፡ ከሚገቡት ፡ ወገን ፡ አይሁኑ ። በነዚህም ፡ ላይ ፡ የሚጨመረው ፡ በደሉ ፡ የታወቀውን ፡ ሰው ፡ ምስክር ፡ ከመሆን ፡ ይከለከሉት ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ዕቁባት ፡ እንደመያዝ ፡ እንደ ፡ ሰካር ፡ እንደ ፡ ተላላቆች ፡ ሥራዎች ፡ አደርጎ ፡ በጥቃቅኑ ፡ (በታናናሾቹ) ፡ በቅልቦሽና ፡ በገበጣ ፡ በቁማርና ፡ ከጐዳና ፡ ላይ ፡ በሰንጠረዥ ፡ እንደለመደ ፡ በገበያም ፡ እንደሚበላ ፡ መልኩ ፡ ባልሆነም ፡ መልክ ፡ እንደሚመስል ፡ (እንደሚታይ) ፡ ያለ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ እንደሚነቀስ ፡ ወይም ፡ የወታደር ፡ ልብስ ፡ እንደሚለብስ ፡ ካህን ፡ ያለ ፡ ነው ።

፩ሺ፰፻፹፩ ሥርዋጽ ። ወብእሲውከስ ፡ ወኢነዳይ ፡ ይኤምር ፡ ኀበ ፡ ጽኑስ ፡ ዘይስእል ፡ ምጽዋተ ፡ ወእስ ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ እንደዩ ፡ ርእሶሙ ፡ በሬትዖሙ ፡ እምንዋይ ፡ ኀላፊ ፡ ለረኪበ ፡ ብዕል ፡ ዘይመጽእ ።

፩ሺ፰፻፹፩ ሥርዋጽ ። ድኃ ፡ እየመሰከር ፡ ማለቱ ፡ ግን ፡ ምጽዋትን ፡ ወደሚለምን ፡ ድኃ ፡ ያመለክታል ። የሚመጣውን ፡ ብዕል ፡ ለማግኘት ፡ በፈቃዳቸው ፡ ራሳቸውን ፡ ከኅላፊው ፡ ገንዘብ ፡ ስለአስቸገሩ ። ሰዎች ፡ ግን ፡ እየደለም ።

፩ሺ፰፻፹፪ ራብዕ ፡ በእንተ ፡ ኊልቈ ፡ ሰማዕት ፡ እለ ፡ ይከውኑ ፡ ስምዐ ፡ ወእመ ፡ ሐጸ ፡ ይኩኑ ፡ ፫ተ ፡ አው ፡ ፪ተ ፡ እስመ ፡ በእፉ ፡ ፪ቱ ፡ ሰማዕት ፡ አው ፡ ፫ቱ ፡ ይቀውም ፡ ኵሉ ፡ ነገር ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ እምላክ ፡ በ፪ቱ ፡ ኪዳናት ፡ ዘውእቶሙ ፡ ኦሪት ፡ ወወንጌል ፡ ናሁ ፡ ይትኄየሉ ፡ ወይፈድፍዱ ፡ ኊልቆ ።

፩ሺ፰፻፹፪ አራተኛው ፡ ምስክር ፡ ስለሚሆኑ ፡ ምስክሮች፡ ቍጥር ፡ ይናገራል ። ቢያንስ ፡ ፫ ፡ ወይም ፡ ፪ ፡ ይሁኑ ። ነገር ፡ ሁሉ ፡ በ፪ ፡ ወይም ፡ በ፫ ፡ ምስክር ፡ ይጸናልና ። ጌታ ፡ በ፪ቱ ፡ ሕጎች ፡ እንደ ተናገረ ። (ዘዳ ፡ ፲፱ ፡ ፲፭ ። ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፲፮ ።) እነዚህም ፡ ኦሪትና ፡ ወንጌል ፡ ናቸው ። እነሆ ፡ ይጠበቁ ። ቍጥርም ፡ ይብዛ ።

፩ሺ፰፻፹፫ ድስቅ ፡ ፯ቱ ፡ ወኢይትወከፉ ፡ ስምዐ ፡ ፩ዱ ፡ ዘእንበለ ፡ ፫ቱ ፡ ወኢ ፡ ዘየሐ... ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘስምዐ ፡ ኮንዎሙ ፡ ከመ ፡ ምግባሮሙ ፡ ሠናይ፡ እምእመ ፡ ንእሶሙ ። በስ ፡ ፹ወ፪ቱ ፡ ኢያሥምርከሙ ፡ ቃለ ፡ ሐሰት ።

፩ሺ፰፻፹፫ ድስቅ ፡ ፯ ። ከ፫ና ፡ ከእነርሱ ፡ ከሚያንስ ፡ ከ፪) ፡ በቀር ፡ ፩ ፡ ምስክር ፡ አይቀበሉ ። ከትንሽነታቸው ፡ ጀምሮ ፡ ምግባራቸው ፡ ደግ ፡ እንደ ሆነ ፡ ምስክር ፡ የሆኑላቸው ፡ ይሁኑ ። በስ ፡ ፹፪ ፡ የሐሰት ፡ ነገር ፡ ደስ ፡ አያሰኛችሁ ።

፩ሺ፰፻፹፬ ጠስ ፡ ዘጽወጊቱ ፡ ወይኩኑ ፡ እለ ፡ ስምዐ ፡ ይከውኑ ፡ በጊዜ ፡ ሊቃሕ ፡ ዕዳ ፡ ፳ተ ፡ ዘ፱ወ፩ዱ ፡ ወእለ ፡ ይከውኑ ፡ ስምዐ ፡ በሐራ ፡ ትእዛዝ ፡ ይኩኑ ፡ ፯ተ ፡ አው ፡ ፳ተ ።

፩ሺ፰፻፹፬ ጠስ ፡ ፳፯ ። በብድር ፡ ዕዳ ፡ ጊዜ ፡ ምስክር ፡ የሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ፳ ፡ ይሁኑ ። ፶፩ ። ትእዛዝ ፡ በመጻፍ ፡ ጊዜ ፡ ምስክር ፡ የሚሆኑ ፡ ፯ ፡ ወይም ፡ ፳ ፡ ይሁኑ ።

፩ሺ፰፻፹፭ ኃምስ ፡ በእንተ ፡ ሥርዓተ ፡ ዕድሜ ፡ ወአብሖተ ፡ ጥያቄ ፡ ወአቅሞቶ ፡ ሰማዕት ። ጠስ ፡ ዘጽወ፩ዱ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ በኵሉ ፡ ዕለት ፡ ዘየሐውሩ ፡ ቦቱ ፡ ምኅኔ ፡ ሐዋር ፡ ዘዕውቅ ፡ ወኑኀ ፡ ፍኖት ፡ ወዕለተ ፡ ተእምኖ ፡ ወዕለተ ፡ አብጽሖ ፡ ለዘይሬሕቅ ፡ ከመ ፡ ይቅም ፡ ሰማዕታተ ፡ ከመ ፡ ይሥራዕ ፡ ሎሙ ፡ ዘይሬሕቅዎ ፡ እምሲሳይ ።

፩ሺ፰፻፹፭ ፭ኛው ፡ ስለቀጠሮው ፡ ሥርዓትና ፡ ስለ ፡ ማስረጃው ፡ ማድረስ ፡ ምስክርም ፡ ስለመጥራት ፡ ይናገራል ። ጠስ ፡ ፳፩ ። ምስክር ፡ ይጠራ ፡ ዘንድ ፡ ለሚወድ ፡ ሰው ፡ በሚሄዱበት ፡ ሁሉ ፡ የታወቀ ፡ የመሄጃውን ፡ ልክና ፡ የመንገዱን ፡ ርዝመት ፡ የመተማመኛውን ፡ ቀንና ፡ የማድረሻውን ፡ ቀን ፡ ከምግብም ፡ ወገን ፡ የሚሸትን ፡ ይወስንላቸው ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ።

አንቀጽ ፡ ፵፫ ።

፩ሺ፰፻፹፮ ሳድስ ፡ በእንተ ፡ ዘኢትከውን ፡ አማነ ፡ ስምዖሙ ፡ ለሰብኢ ፡ ወላዕሌሆሙ ፡ ኢይደሉ ፡ ስምዐ ፡ ብእሲ ፡ ለርእሱ ፡ በቃሉ ፡ ባሕቲቱ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ "እመሰ ፡ ስልየ ፡ ስምዐ ፡ ኮንኩ ፡ ለርእስየ ፡ ኢኮነ ፡ ጽድቀ ፡ ስምዕየ" ። ወብዝሎቱ ፡ በእንተ ፡ ከዊነ ፡ ንጹሐ ፡ እንትሙሰ ፡ ታጸድቁ ፡ ርእስክሙ ፡ ወእግዚአብሔር ፡ የአምር ፡ አልባቢክሙ ።

፩ሺ፰፻፹፯ ጠስ ፡ ሺወ፺፱ ፡ ወኢይደልዎ ፡ ለብእሲ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ስምዐ ፡ ለእሊአሁ ፡ ወይትዐወቅ ፡ ኢይኩን ፡ ስምዐ ፡ ብእሲ ፡ ለወልዱ ፡ ወኢ ፡ ለወልደ ፡ ወልዱ ፡ ወለእለ ፡ ይትኃሰቁ ፡ እምታሕቴ ፡ እሉ ፡ ኢ ፡ ለአቡሁ ፡ ወኢ ፡ ለእሙ ፡ ወኢ ለእምኄሙ ። ወእለ ፡ መልዕልቶሙ ፡ ኢለብእሲቱ ፡ ወኢ ፡ ለእኁሁ ፡ ወኢ ፡ ለእኅቱ ፡ ወኢ ፡ ለገብሩ ፡ ወኢ ፡ ለስታፌሁ ፡ በዘሀለዎሙ ፡ እምተሳትፎ ፡ ወኢ ፡ ለዘአጽሐፈ ፡ ትእዛዘ ፡ በእንቲአሁ ፡ ዘእንበለ ፡ ለዘውምሮ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ዘይከውን ፡ ስምዐ ፡ ላዕሌሁ ፡ እው ፡ ኮነ ፡ ዘስምዐ ፡ ይከውንዎ ፡ ሰራዊት ፡ በዘመደ ፡ ምስለ ፡ ስማዕት ፡ ዘከመ ፡ ፪ቱ ፡ ውሉድ ፡ ወዘከመ ፡ ፪ቱ፡ እምኀዋን ። ወይደሉ ፡ ስምዖሙ ፡ ላዕለ ፡ እለ ፡ ዘከርነ ፡ ለመንፈቆሙ ፡ ወለካልኣኒሆሙ ።

፩ሺ፰፻፹፰ ጠስ ፡ ዘሺወ፺፱ ፡ ወኢይኩን ፡ ስምዐ ፡ በእንተ፡ ጽሒፈ ፡ ትእዛዝ ፡ ዘውእቱ ፡ ወራሲ ፡ ኪያሁ ፡ ዘሀለወ ፡ ስሙ ፡ ለተዋርሶ ፡ በውስቴታ ፡ እው ፡ ዘተአዘዘ ፡ ሎቱ ፡ ወኢይደሉ ፡ ስምዐ ፡ ገብር ፡ ለእግዚኡ ፡ ዘአግዓዞ ፡ ወኢ ፡ ለወልደ ፡ እግዚኡ

፩ሺ፰፻፹፱ ድስቅ ፡ ዘ፩ቱ ፡ በስ ፡ ዘ፺ወ፪ቱ ፡ ወኢይደሉ ፡ ይኩን ፡ ስምዐ ፡ ብእሲ ፡ በላዕለ ፡ ጸላኢቱ ፡ ወኢ፡ ላዕለ ፡ በዓለ ፡ ሰዳሁ ፡ ዘእንበለ ፡ ለእመ ፡ አትደሙ ፡ ወተሞገሱ ፡ በስምዐ ፡ ዘእሁ ፡ ሎሙ ፡ ወላዕሌሆሙ ፡

፩ሺ፰፻፺ ጠስ ፡ ሺወ፺፱ ፡ ወዘኒ ፡ ኮነ ፡ ዐራቄ ፡ ማእከለ ፡ ሰብእ ፡ በ፩ዱ ፡ ግብር ፡ እምግብራት ፡ ኢይክውኖ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ስምዐ ፡ በውእቱ ፡ ግብር ። ወዘስምዐ ፡ ኮነ ፡ ላዕለ ፡ ፩ዱ ፡ ብእሲ ፡ በእንተ ፡ አበሳ ፡ አኮ ፡ ዘይደልዎ ፡ ለዝኩ ፡ ብእሲ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ስምዐ ፡ ላዕለ ፡ ዘኮነ ፡ ስምዐ ፡ በላዕሌሁ። ወዘኒ ፡ ያስተባእስ ፡ ወያስተሳልም ፡ በምንትኒ ፡

ስለ ፡ ዳኛ ።

፩ሺ፰፻፹፮ ስድስተኛው ፡ ምስክርነታቸው ፡ ለእርሱና ፡ በእነርሱም ፡ ላይ ፡ እውነት ፡ ስለማትሆን ፡ ይናገራል ። የሰው ፡ ምስክርነት ፡ ለራሱ ፡ በቃሉ ፡ ብቻ ፡ አይገባም ። ምስጋና ፡ ይግባውና፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እኔ ፡ ለራሴ ፡ ምስክር ፡ ብሆን ፡ ምስክርነቴ ፡ እውነት ፡ አይሆንም ፡ እንዳለ ። (ዮሐ ፡ ፭ ፡ ፴፩) ። ስለንጽሕናም ፡ ሁናቴ ፡ እናንተስ ፡ ራሳችሁን ፡ ጻድቃን ፡ ታደርጋላችሁ ። እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ልቡናችሁን ፡ ያውቃል ፡ በማለቱ ፡ ነው ።

፩ሺ፰፻፹፯ ጠስ ፡ ሺ፺ ። ሰው ፡ ለወገኖቹ ፡ ምስክር ፡ ሊሆን አይገባውም ። ሰው ፡ ለልጁ ፡ ወይም ፡ ለልጅ ፡ ልጁ ፡ ከእነዚህ ፡ በታችም ፡ ለሚቈጠሩት ፡ ለአባቱና ፡ ለእናቱ ፡ ወይም ፡ ለአያቱ ፡ ወደላይም ፡ ለእሉት ፡ ለሚስቱ ፡ ለወንድሙም ፡ ለእኅቱም ፡ ወይም ፡ ለባሪያው ፡ ከሽርክነት ፡ ወገን ፡ ስላላቸው ፡ ለሽሪኩም ፡ ወይም ፡ ስለእርሱ ፡ ትእዛዝ ፡ ለጻፈለት ፡ ሰው ፡ ምስክር ፡ እንዳይሆን ፡ ይታወቃል ። ምስክር ፡ የሚሆኑበት ፡ ሰው ፡ ለሚወደው ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ወይም ፡ ምስክር ፡ የሚሆኑለት ፡ ሰው ፡ ከምስክሮች ፡ ጋር ፡ በዝምድና ፡ የተካከለ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ይኸውም ፡ እንደ ሁለት ፡ ልጆችና ፡ እንደ ፡ ሁለት ፡ አያቶች ፡ ያሉናቸው ። በጠቀስናቸው ፡ ላይ ፡ ለእኩሌቶቹና ፡ ስሌሎቻቸውም ፡ ምስክርነታቸው ፡ ይገባል ።

፩ሺ፰፻፹፰ ጠስ ፡ ሺ፺ ። ማዘዣ ፡ ስለመጻፍ ፡ ምስክር ፡ አይሁን ። ይኸውም ፡ ለመውረስ ፡ ስሙ ፡ በውስጧ ፡ ያለ ፡ እርሷን ፡ የሚወርሰው ፡ ወይም ፡ የታዘዘለት ፡ ሰው ፡ ነው ። የባሪያ ፡ ምስክርነት ፡ ነፃ ፡ ለአወጣው ፡ ለጌታው ፡ ወይም ፡ ለጌታው ፡ ልጅ ፡ አይገባም ።

፩ሺ፰፻፹፱ ድስቅ ፡ ፩ ። በስ ፡ ፺፪ ። አስቀድመው ፡ ለእነርሱና ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ በምስክርነቱ ፡ ካልተስማሙ ፡ በቀር ፡ ሰው ፡ በጠላቱ ፡ ላይና ፡ በባለዕዳው ፡ ላይ ፡ ምስክር ፡ ሊሆን ፡ አይገባም ።

፩ሺ፰፻፺ ጠስ ፡ ሺ፺ ። ከሥራ ፡ በአንድ ፡ ሥራ ፡ በሰው ፡ መካከል ፡ አስታራቂ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ ሥራ ፡ ምስክር ፡ ሊሆን ፡ አይገባም ። በአንድ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ስለበደል ፡ ምስክር ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ምስክር ፡ በሆነበት ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ምስክር ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ለዚያ ፡ ሰው ፡ የሚገባው ፡ አይደለም ። በማናቸውም ፡ ሥራ ፡ የሚያጣላና ፡

አንቀጽ ፡ ፵፫ ።

ግብር ፡ ኢያያልዎ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ስምዐ ፡ በውእቱ ፡ ግብር ። ወለኵሉ ፡ ዘይደሉ ፡ ስምዐ ፡ ዚአሁ ፡ ይከውን ፡ ስምዑ ፡ ርቱዐ ፡ በላዕለ ፡ ነፍሱ ፡ ይደሉ ፡ ስምዑ ፡ በላዕሌሁ ።

፩ሺ፭፻፲፩ ረስጠብ ፡ ፶ወ፪ቱ ፡ ወኢይትወከፉ ፡ ስምዐ ፡ ዕልዋን ፡ ላዕለ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወኢይትወከፉ ፡ ላዕሌሁ ፡ ስምዐ ፩ዱ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እምኤጲስ ቆጶሳት ።

፩ሺ፭፻፲፪ ጠስ ፡ ፷ወ፪ቱ ፡ ወናሁ ፡ ተከልአ ፡ እምከዊነ ፡ ስምዕ ፡ ዘስምዐ ፡ ኮነ ፡ በጽሒፈ ፡ ትእዛዝ ፡ ዘኢይደሉ ፡ እስከ ፡ ያስተጻንዖ ፡ ወሕግኒ ፡ ኢያኤዝዞ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ስምዐ ፡ ወእምር ፡ ከመ ፡ እምዝንቱ ፡ ይትዐወቅ ፡ እስመ ፡ ከዊነ ፡ ስምዕ ፡ ከመ ፡ እምነት ፡ እንተ ፡ ማኅፀንት ፡ ይእቲ ፡ ለዘ ስምዐ ፡ ይከውኑ ፡ ሎቱ ፡ በኀበ ፡ ስማዕቱ ፡ መፍትው ፡ የሀቦ ፡ ሎቱ ፡ ላዕሌሁ ፡ አመ ፡ ኀሠሠ ፡ ኪያሁ ፡ ከመ ፡ ትኩኖ ፡ ለበቍዔት ፡ ወዘሂ ፡ ኢወሀቦ ፡ ረስዮ ፡ ብዑለ ፡ እምጸጋሁ ፡ ኢይደልዎ ፡ ኀሢሠ ፡ ዓስብ ፡ በእንቲአሃ ፡ ኢ ፡ በእንተ ፡ ዘአንበራ ፡ ኀቤሁ ፡ ወኢ ፡ በእንተ ፡ ኅሢአታ ።

፩ሺ፭፻፲፫ ሳብዕ ፡ በእንተ ፡ ስምዐት ፡ እለ ፡ ኢይትአመንዎሙ ። ጠስ ፡ ፷ወ፯ቱ ፡ ስምዐት ፡ እለ ፡ ይከውና ፡ እምብእሲ ፡ ኀላፌ ፡ ፍኖት ፡ ወዘይመስል፡ ኪያሃ ፡ ኢይቀውም ፡ ምንትኒ ፡ እምኔሃ ፡ ግሙራ፡ ዘከመ ፡ ይብል ፡ አሐዱ ፡ እንሰ ፡ ሀሎኩ ፡ ኀበ ፡ እገሌ ፡ ውስተ ፡ ግብር ፡ ወሰማዕኩ ፡ እገሌሃ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ነሥአ ፡ እምእገሌ ፡ ከመዝ ፡ ወከመዝ ፡ እስመ ፡ ዛቲ ፡ ስምዕ ፡ ኢኮነት ፡ እምአእምሮ ፡ ወኢኮነት ፡ ድሉተ ፡ ለተወክፎ ።

፩ሺ፭፻፲፬ መጅ ፡ ፰ ፡ ወኢትቀውም ፡ ስምዕ ፡ በትኀይልት ፡ ዘእንበለ ፡ እምድኅረ ፡ ይትዓወቁ ፡ ስማዕት ፡ ዘስምዐ ፡ ይከውኑ ፡ ቦቱ ፡ ወየሐትቱ ፡ በእንቲአሁ ፡ ወይበጽሑ ፡ ኀበ ፡ ጥያቄሁ ።

፩ሺ፭፻፲፭ ሳምን ፡ በእንተ ፡ ተማኅሦ ፡ እምስምዐ ፡ ሐሰት ፡ ወዘከመ ፡ ይረክቦ ፡ ዕዳ ፡ ለስማዕተ ፡ ሐሰት፡ በስምዕ ፡ ርቱዕ ፡ እምቅመተ ፡ ስምዑ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢትኩን ፡ ስምዐ ፡ በሐሰት ።

፩ሺ፭፻፲፮ ትሑ ፡ ፲ወ፬ቱ ፡ በስ ፡ ፷ወ፱ቱ ፡ ወእመቦ ፡ ዘስምዐ ፡ ኮነ ፡ ላዕለ ፡ አሐዱ ፡ በዘይሠዐር ፡ እመ

ስለ ፡ ዳኛ ።

የሚያፋቅርም ፡ ሰው ፡ በዚሀ ፡ ሥራ ፡ ምስክር ፡ ሊሆን ፡ አይገባውም ። ምስክርነቱ ፡ የሚገባ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ምስክርነቱ ፡ እውነት ፡ ይሆናል ። በራሱ ፡ ላይ ፡ ሊመሰክር ፡ ይገባል ።

፩ሺ፭፻፲፩ ረስጠብ ፡ ፶፪ ። በኤጲስቆጶስ ፡ ላይ ፡ የወንጀለኞችን ፡ ምስክርነት ፡ አይቀበሉ ። ከኤጲስቆጶሳትም ፡ የአንድ ፡ ኤጲስቆጶስን ፡ ምስክርነት ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ አይቀበሉ ።

፩ሺ፭፻፲፪ ጠስ ፡ ፷፪ ። የማይገባ ፡ ትእዛዝን ፡ በመጻፍ ፡ ምስክር ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ እስኪያጸናው ፡ ድረስ ፡ ምስክር ፡ ከመሆን ፡ እነሆ ፡ ተከለከለ ። ሕግም ፡ ምስክር ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ አያዝዝለትም ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ እንዲታወቅ ፡ እወቅ ። ምስክር ፡ መሆን ፡ ምስክር ፡ ለሚሆኑት ፡ በምስክሩ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ አደራ ፡ መተማመን ፡ ናትና ። ለጥቅም ፡ ትሆነው ፡ ዘንድ ፡ እርሱን ፡ በፈለገው ፡ ጊዜ ፡ ያስበትን ፡ አደራ ፡ ለእርሱ ፡ ሊሰጠው ፡ ይገባል ። ባይሰጠውም ፡ ከገንዘቡ ፡ ባዶ ፡ አደረገው ። በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ስለአስቀመጣት ፡ ስለአልወሰዳትም ፡ ስለእርሱዋ ፡ ዋጋ ፡ መፈለግ ፡ አይገባውም ።

፩ሺ፭፻፲፫ ፯ኛው ፡ ስለማያምኑባቸው ፡ ምስክርነቶች ፡ ይናገራል ። ጠስ ፡ ፷፯ ። ከመንገደኛ ፡ ሰውና ፡ እርሷን ፡ ከሚመስል ፡ የሆኑ ፡ ምስክርነቶች ፡ ከእርሱዋ ፡ የተነሣ ፡ ፈጽሞ ፡ በማናቸውም ፡ አይጸናም ። አንዱ ፡ እንዲህ ፡ እንደሚል ፡ እኔ ፡ ከእገሌ ፡ ዘንድ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ነበርኩ ። እገሌን ከእገሌ ፡ ዘንድ ፡ እርሱ ፡ እንደዚህና ፡ እንደዚህ ፡ እንደ ፡ ወሰደ ፡ ሲናገር ፡ ሰማሁ ። ይህች ፡ ምስክርነት ፡ ከማወቅ ፡ አይደለችምና ፡ ለመቀበል ፡ የተገባች ፡ አይደለችም ።

፩ሺ፭፻፲፬ መጅ ፡ ፰ ። ምስክርነት ፡ በኀይል ፡ አትጸናም ። ምስክር ፡ የሚሆኑበትን ፡ ነገር ፡ ምስክሮች ፡ ስለእርሱ ፡ መርምረው ፡ ቢያውቁ ፡ ነው ፡ እንጂ ወደ ፡ እርግጡም ፡ ይድረሱ ።

፩ሺ፭፻፲፭ ስምንተኛው ፡ በሐሰት ፡ ከመመስከር ፡ ስለ መራቅና ፡ በሐሰት ፡ የመሰከረውን ፡ ከምስክርነቱ አቅዋም ፡ የተነሣ ፡ በእውነተኛ ፡ ምስክር ፡ ዕዳ ፡ እንዲያገኘው ፡ ይናገራል ። እግዚአብሔር ፡ በሐሰት ፡ ምስክር ፡ አትሁን ፡ አለ ። (ዘዳ ፡ ፮ ፡ ፳)።

፩ሺ፭፻፲፮ ትሄ ፡ ፲፬ ። በስ ፡ ፷፱ ። በአንዱ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ከመዓርጉ ፡ በሚሻር ፡ ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ለቅ

አንቀጽ ፡ ፵፫ ።

ዓርጊሁ ፡ እው ፡ ይትረሰይ ፡ ውስተ ፡ ሁንጌ ፡ ወእምዝ ፡ ተዐውቀ ፡ ስምዐ ፡ ሐሰቱ ፡ ይትኩ ንን ፡ በሁንጌ ፡ ዘፈትሐ ፡ ቦቱ ፡ ላዕለ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ዘኮነ ፡ ስምዐ ፡ በሐሰት ፡ በላዕሌሁ ።

፩ሺ፰፻፲፯ ታስዕ ፡ በእንተ ፡ ግብር ፡ እንተ ፡ ታወፅእ ፡ እምከዊነ ፡ ስምዕ ፡ ወዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ፀእት ፡ እም ትእዛዛት ፡ ድልዋት ፡ ወበእት ፡ ውስተ ፡ ግብ ራት ፡ ካልእት ። ጠሰ ፡ ዘ፳ወ፯ቱ ፡ ወኢይኩን ፡ ስምዐ ፡ ዘዘለፍዎ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ነሥአ ፡ ንዋየ ከመ ፡ ይኩን ፡ ስምዐ ፡ በሐሰት ፡ ወመፍትው ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ እስተጻንዖተ ፡ ስምዕ ፡ ለዘይከ ውን ፡ ስምዐ ፡ ወፀእቱ ፡ እምኔሃ ፡ ገሃደ ።

፩ሺ፰፻፲፰ ዓሥር ፡ በእንተ ፡ ስምዕ ፡ በዲበ ፡ ስምዕ ። ኢይደሉ ፡ ስምዕ ፡ ዲበ ፡ ስምዕ ፡ ዳእሙ ፡ ሶበ ፡ ይቤሎ ፡ ስማዕት ፡ ቀዳማዊ ፡ ለስማዕት ፡ ዳኅ ራዊ ፡ ስምዐ ፡ ኩን ፡ በላዕለ ፡ ስምዕየ ፡ ወይእቲ ፡ ከመዝ ፡ ወከመዝ ፡ ወእምከመ ፡ ርእዮ ፡ ዳኅ ራዊ ፡ ወነሥኦ ፡ ስምዐ ፡ ኮነ ፡ በነበ ፡ ፈታሒ ፡ በስምዑ ፡ ወተጠየቀ ፡ ኪያሃ ፡ ይከውን ፡ ስምዐ ፡ በላዕሌሃ ፡ ወለእመኒ ፡ ኢኀደጎ ፡ ይኩን ፡ ስምዐ ።

፩ሺ፰፻፲፱ ወይደሉ ፡ እንከ ፡ ስምዕ ፡ በላዕለ ፡ ስምዕ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ሰማዕት ፡ ቀዳማዊ ፡ ዘይወየ ፡ እው ፡ ዘተሞቅሐ ፡ እው ፡ ነግደ ፡ እው ፡ ሞተ ፡ ወእመሰ ፡ ኢኮነ ፡ ከማሁ ፡ እው ፡ ለእመ ፡ ተጻ ደቆ ፡ ዘየወፅእ ፡ እምከዊነ ፡ ስምዕ ፡ እው ፡ ተበ እሰ ፡ ምስለ ፡ ዘይከውን ፡ ስምዐ ፡ በላዕሌሁ ፡ ወፈድፋደሰ ፡ በዘይከልእ ፡ እምውእቱ ፡ ስምዕ ፡ ኢይከውን ፡ እማን ፡ ወይትመሰሉ ፡ በኵሉ ፡ ሰማዕታት ፡ በስምዕ ፡ ዲበ ፡ ስምዕ ፡ እምድኅረ ፡ ኮኑ ፡ ስምዐ ፡ ፪ቱ ፡ እው ፡ ፫ቱ ።

፩ሺ፰፻፳ ምዕራፍ ፡ ፲ወ፫ቱ ። በእንተ ፡ ፍትሕ ፡ ዘድልው ፡ ለሰማዕት ፡ ወይእቲ ፡ ፫ቱ ፡ እክፋል ። ቀዳ ሚሃ በእንተ ፡ ስምዕ ፡ ላዕለ ፡ ኃጣውእ ። ድስቅ ፡ ፯ቱ ፡ ኢያአምንዎ ፡ ለኵሉ ፡ ሰብእ በከዊነ ፡ ስምዕ ፡ እስመ ፡ ብዙኃን ፡ እምሰብእ ፡ እለ ያስተዋድዩ በሐሰት ቀኒአሙ በእከይ ላዕለ እንዊሆሙ ከመ ፪ቱ ረበናት እለ ኮኑ ስምዐ ላዕለ ሶስና በባቢሎን ። ወእን ተኒ ፡ ኦ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ኩን ፡ ነቂሆ ፡ መንፈስ ፡

ስለ ፡ ዳኛ ።

ጣት ፡ ይዘጋጅ ፡ (ይሰጥ) ፡ ዘንድ ፡ ምስክር ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ምስክር ነቱ ፡ ቢታወቅ ፡ በሐሰት ፡ ምስክር ፡ በሆነበት ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ በፈረዱት ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣ ። (ዘዳ ፡ ፲፱ ፡ ፲፭ - ፳) ።

፩ሺ፰፻፲፯ ዘጠኝኛው ፡ ምስክር ፡ ከመሆን ፡ ስለም ታወጣ ፡ ሥራ ፡ ይናገራል ። ይዘችም ፡ ከሚ ገቡ ፡ ትእዛዛት ፡ ወጥቶ ፡ ወደሌሎች ፡ ሥራዎች መግባት ፡ ነው ። ጠሰ ፡ ፳፯ ። በሐስት ፡ ሊመሰ ክር ፡ ገንዘብ ፡ እንደተቀበለ ፡ ተገኝቶ ፡ የቀጡት ሰው ፡ ምስክር ፡ አይሁን ። ምስክር ፡ ለሚሆነው ሰው ፡ ምስክርነቱን ፡ ማስጠናት ፡ ይሆን ፡ ዘንድ የሚገባ ፡ ነው ። ከእርሷም ፡ መውጣቱ ፡ ግልጽ ፡ ይሁን ።

፩ሺ፰፻፲፰ ፲ኛው ፡ በምስክር ፡ ላይ ፡ ስለምስክር ፡ ይናገ ራል ። በምስክር ፡ ላይ ፡ ምስክር ፡ አይገባም ። የፊተኛው ፡ ምስክር ፡ የኋለኛውን ፡ ምስክር ፡ በምስክርነቴ ፡ ላይ ፡ መስክር ፡ ቢለው ፡ ነው ፡ እንጂ ። ይህችም ፡ እንዲህና ፡ እንዲህ ፡ ናት ። ኋለኛው ፡ ከተመለከተው ፡ በዳኛም ፡ ዘንድ ፡ በምስክርነቱ ፡ ላይ ፡ እነሆ ፡ ምስክር ፡ ከሆነ ፡ እርሷንም ፡ ከተረዳ ፡ በእርሱዋ ፡ ላይ ፡ ምስክር ፡ ይሆናል ። ባይተወውም ፡ ምስክር ፡ ይሁን ።

፩ሺ፰፻፲፱ መጀመሪያው ፡ ምስክር ፡ የታመመ ፡ ወይም ፡ የታሰረ ፡ ወይም ፡ እሩቅ ፡ አገር ፡ የሄደ ፡ ወይም ፡ የሞተ ፡ ቢሆን ፡ እንግዲህ ፡ በምስክር ፡ ላይ ፡ ምስክር ፡ ይገባል ። እንዲህ ፡ ባይሆን ፡ ግን ፡ ከምስክርነት ፡ የሚያወጣው ፡ ነገር ፡ ድንገት ፡ ቢያገኘው ፡ ወይም ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ምስክር ፡ ከሚሆንበት ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ይልቁንም ፡ ከዚህ ፡ ምስክርነት ፡ በሚከለክለው ፡ ነገር ፡ ቢጣላ ፡ ምስክርነቱ ፡ እውነተኛ ፡ አይሆንም ። ፪ ፡ ወይ ም ፡ ፫ ፡ ምስክር ፡ ከሆኑ ፡ በኋላ ፡ በምስክር ፡ ላይ ምስክር ፡ በምስክሮች ፡ ቍጥር ፡ ይተኩ ።

፩ሺ፰፻፳ ምዕራፍ ፡ ፲፫ ፡ ለምስክሮች ፡ ስለሚገባው ፡ ፍርድ ፡ ይናገራል ። ይዘችም ፡ ስምንት ፡ ክፍል ፡ ናት ። መጀመሪያዋ ፡ በኃጢአቶች ፡ ላይ ፡ ስለመ መስከር ፡ ነው ። ድስቅ ። ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ምስክር በመሆን ፡ አይመኑት ። በወንድሞቻቸው ፡ ላይ ፡ በተንኰል ፡ ቀንተው ፡ በሐሰት ፡ ነገር ፡ የሚ ሠሩ ፡ ከሰዎች ፡ ወገን ፡ ብዙዎች ፡ ናቸውና ። ሁለቱ ፡ ረበናት ፡ በባቢሎን ፡ በሶስና ፡ ላይ ፡ ምስክር ፡ እንደሆኑባት ። ኤጲስቆጶስ ፡ ሆይ ፡

በዛቲ ፡ ምግባራት ፡ ከመ ፡ ብእሴ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢታስትት ፡ በተወክፎ ፡ ስምዐ ፡ ለዘከመዝ ፡ ውእቱ ፡ ወኢታኅጉሎ ፡ ለዘኢአበሰ ፡ ወኢታቅትሎ ፡ ለጻድቅ ።

፩ሺ.፳፻፳፩ ዳግም ፡ በእንተ ፡ ዘይደሉ ፡ ብጽሐቶሙ ፡ ለአብጽሖተ ፡ ስምዕ ። ጠሰ ፡ ፳ወ፯ ፡ እለ ፡ ይከውኑ ፡ ስምዐ ፡ በእንተ ፡ መጻሕፍተ ፡ ዕዳ ፡ ለቃሕ ፡ ይደልዎሙ ፡ ይበሉ ፡ ከመ ፡ እሙንቱ ፡ ነበሩ ፡ አመ ፡ ተመጥዎተ ፡ ንዋይ ፡ ወከመ ፡ ተአምኖቱ ፡ ኮነት ፡ በሀልዎቶሙ ፡ በከመ ፡ ይደሉ ፡ በውስተ ፡ ሕግ ፡ ወከመ ፡ እሙንቱ ፡ ለዛቲ ፡ ግብር ፡ ባሕቲታ ፡ ተጸውዑ ። ወበጊዜ ፡ ዕጸባ ፡ ወተንሕልዎ ፡ ከመ ፡ ይብጽሑ ፡ ሰማዕት ፡ ለሊሆሙ ወአኮ ፡ ቃለ ፡ በምፆሙ ፡ ባሕቲታ ፡ አስመ ፡ ኀበ ስምፆሙ ፡ እለ ፡ ይከውኑ ፡ ሰምዐ ፡ ያፀምዑ ፡ ወአኮ ፡ ኀበ ፡ ሀልዎቶሙ ፡ እስመ ፡ ስምዑ ፡ ለብእሲ ፡ ያማኅሥ ፡ እምኔሁ ፡ ሐሜተ ።

፩ሺ.፳፻፳፪ ሣልስ ፡ በእንተ ፡ ኢተሰናአዎቶሙ ። ጠሰ ፡ ፳ወ፯ቱ ፡ ወእምከመ ፡ ኢኀብረ ፡ ቃለ ፡ ሰማዕታት ፡ በበይናቲሆሙ ፡ አው ፡ ተጋዐዘ ፡ ፩ዱ ፡ ምስለ ፡ ፩ዱ ፡ እምሰማዕታት ፡ አው ፡ ኮነ ፡ ስምፆሙ ፡ በሐሰት ፡ ይደልዎ ፡ ለፈታሒ ፡ ከመ ፡ ይትወከፎሙ ፡ ለእለ ፡ እሙን ፡ ቃሎሙ ፡ እምውስቴቶሙ ፡ ወይቅሥፎሙ ፡ ለሐሳውያን ፡ ለእመ ፡ ተሀውቀ ፡ ከመ ፡ እሙንቱ ፡ ልሙዳን ፡ ለአሕሥሞ ፡ ግብር ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ መብዝኅቶሙ ፡ ለሰማዕት ፡ በ፩ዱ ፡ ቃል ፡ ወቦ ፡ እለ ፡ ተፈልጡ፡ እምኔሆሙ ፡ ኢያዕምዑ ፡ ኀበ ፡ መብዝኅቶሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ኀበ ፡ ዘይሰነአወ ፡ ወዘኢኮነ ፡ እምኔሆሙ ፡ በተጸልአ ፡ አው ፡ በተፋቅሮ ። ወበምሀ ፡ ይኩኑ ፡ ሎቱ ፡ ፈታሒ ፡ ወእለ ፡ ሀለዉ ፡ እስመ ፡ ኢመፍትው ፡ ከመ ፡ ይአመንዎሙ ፡ ለሰማዕት ፡ በእንተ ፡ ብዝኆሙ ፡ አላ ፡ በእንተ፡ ሃይማኖት ፡ ወጽድቀ ፡ ቃል ።

፩ሺ.፳፻፳፫ ወይደሉ ፡ ከመ ፡ ይትሐተት ፡ ግብሮሙ ፡ ለኵሉ ፡ ሰማዕት ፡ ለእመኒ ፡ ክቡር ፡ ውእቱ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ነውር ፡ አው ፡ ኅሱር ፡ ውእቱ ፡ ዘየሐምዮዎ ፡ አው ፡ ባዕል ፡ አው ፡ ጽኑስ ፡ ዘይትሔዘብዎ ፡ በምንትኒ ፡ እምተዓድዎ ፡ በኀሢሠ ፡ ረባኅ ፡ ለእመኒ ፡ ዓርኩ ፡ ውእቱ ፡ ለመስተዓርር አው ፡ ፀሩ ፡ ውእቱ ፡ ለዘይዓረሮ ። ወእምከመ ፡ ድኅነ ፡ በሐረቱ ፡ እምነውር ፡ ይደሉ ፡ ስምዑ ፡



አንተም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ እንደመሆንህ ፡ በዚህች ፡ ሥራ ፡ ልበ ፡ ሰፊ ፡ ሁን ። እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ምስክርነት ፡ መቀበልን ፡ አታቃልል ። ያልበደለውን ፡ አታጥፋው ። ጻድቁንም ፡ አታስገድለው ።

፩ሺ.፳፻፳፩ ፪ኛው ፡ ምስክርነትን ፡ ለማድረስ ፡ መድረስ ፡ ስለሚገባቸው ፡ ይናገራል ። ጠሰ ፡ ፳፯ ። ስለብድር ፡ ዕዳ ፡ ደብዳቤ ፡ ምስክር ፡ የሚሆኑ ፡ ሰዎች ገንዘብ ፡ በመቀበል ፡ ጊዜ ፡ እነርሱ ፡ እንደነበሩ ፡ በሕግ ፡ እንደሚገባው ፡ አምነቱ ፡ እነርሱ ፡ ባሉበት ፡ እንደሆነች ፡ እነርሱም ፡ ለዚች ፡ ሥራ ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ተጠሩ ፡ ሊናገሩ ፡ ይገባቸዋል ። በጭንቅና ፡ በተንኰል ፡ ጊዜ ፡ ምስክሮች ፡ ራሳቸው ፡ ይደርሱ ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ። የምስክርነት ፡ ቃላቸው ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። በሚኖሩበት ፡ ቦታ ፡ ያይደለ ፡ በምስክርነታቸው ፡ ዘንድ ፡ ምስክር ፡ የሚሆኑትን ፡ ያዳምጣሉና ። የሰው ፡ ምስክርነቱ ፡ ሐሜትን ፡ ከራሱ ፡ ያርቃልና ።

፩ሺ.፳፻፳፪ ፫ኛው ፡ ስለ ፡ አለመስማማታቸው ፡ ይናገራል ። ጠሰ ፡ ፳፯ ። የምስክሮች ፡ ቃል ፡ እርስበርሳቸው ፡ ባይተባበር ፡ ወይም ፡ ከምስክሮች ፡ አንዱ ፡ ከአንዱ ፡ ጋር ፡ ቢከራከር ፡ (ቢለያዩ) ፡ ወይም ፡ ምስክርነታቸው ፡ በሐሰት ፡ ቢሆን ። ለዳኛ ፡ ከእነርሱ ፡ ውስጥ ፡ ቃላቸው ፡ የታመነውን ፡ ሊቀበላቸው ፡ ሐሰተኞችንም ፡ እነርሱ ፡ ሥራን ፡ ለማጥፋት ፡ ልማደኞች ፡ እንደሆኑ ፡ ከታወቀ ፡ ሊገርፋቸው ፡ ይገባዋል ። ከምስክሮች ፡ አብዛኛው ፡ በአንድ ፡ ቃል ፡ ቢሆን ፡ ከእነርሱም ፡ የተለዩ ፡ ቢኖሩ ፡ ወደ ፡ ብዙዎቹ ፡ አያዳምጡ ። ወደሚስማሙትና ፡ በጥል ፡ ወደእልሆነው ፡ በፍቅርም ፡ ወደሆነው ፡ እንጂ ። ዳኛውና ፡ ከዚያ ፡ ያሉት ፡ ምስክር ፡ ይሁኑስት ። ምስክሮችን ፡ ስለብዛታቸው ፡ ሊያምኗቸው ፡ አግባብ ፡ አይደለምና ። በለሃይማኖትና ፡ ስለ ቃል ፡ እውነተኛነት ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፩ሺ.፳፻፳፫ ነውር ፡ የሌለበት ፡ ክቡር ፡ ቢሆንም ፡ ወይም የሚታማ ፡ ወራዳ ፡ ወይም ፡ ባለጸጋ ፡ ወይም ፡ ጥቅምን ፡ በመፈለግ ፡ ከመደፋፈር ፡ በማናቸውም ፡ የሚጠረጥሩት ፡ ድኃም ፡ ቢሆን ፡ ለከሳሽ ፡ ወዳጁ ፡ ወይም ፡ ለተከሳሽ ፡ ጠላቱ ፡ ቢሆን ፡ የምስክሮች ፡ ሁሉ ፡ ግብራቸው ፡ ሊመረመር ፡ ይገባል ። በአካሄዱም ፡ ከነውር ፡ ቢድን ፡ ምስክርነቱ ፡ ይገባል ። ምስክሮች ፡ አንድ ፡ ግብር ፡

አንቀጽ ፡ ፵፫ ።

ወለይርአይ ፡ ፈታሒ ፡ ለእመ ፡ ኮኑ ፡ ሰማዕት ፡ ይዜክሩ ፡ ሰዶ ፡ ግብረ ፡ ያውሥእ ፡ በእንተ ፡ ዘይሴእሉ ፡ በእንቲአሁ ፡ በዘይበቍዕ ፡ ወእይ ፡ ይእቲ ፡ እማሬ ፡ ፍኖት ፡ እንተ ፡ ኢይትዌከፍዋ።

፩ሺ፭፻፳፬ ራብዕ ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ይትኅረዩ ፡ ወእለሂ ፡ የኀርይዎሙ ። ጠሰ ፡ ፳ወ፯ቱ ፡ ወለሕፃናት ፡ እእምሮ ፡ እምእለ ፡ ይከውኑ ፡ ሰምዐ ፡ ይፍትንዎሙ ፡ ለእመ ፡ ይፈቅድዎሙ ፡ ወእመኒ ፡ ኮነ ፡ ዘይደሉ ፡ ሰምዐ ፡ ዘእሁ ፡ ለዘኢሀለወ ፡ ኢይትወከፉ ፡ ሰምዖ ፡ ዘእንበለ ፡ ያመክርዎ ።

፩ሺ፭፻፳፭ መ፳ ፡ ፭ ፡ ኢተንጽሕዎ ፡ ለዘኢይደሉ ፡ እንጽሖቱ ፡ ወናሁ ፡ ተጽሕፈ ፡ ዘይቤ ፡ እሌ ፡ ሎቱ ፡ ለዘያነጽሖ ፡ ለእኩይ ፡ በንዋእ ፡ ሕልያን፡ ወያመይጣ ፡ ለፍትሐ ፡ ጽድቅ ፡ እምነዳይ ፡ ወያከልእ ፡ ዘይደልዎ ።

፩ሺ፭፻፳፮ ኃምስ ፡ ጠሰ ፡ ፳ወ፯ቱ ፡ ዘያመጽእ ፡ ሰማዕተ ፡ እምጸላእቱ ፡ ኢይከውኖ ፡ ሎቱ ፡ ሰበ ፡ ይበጽሖ ፡ ውስተ ፡ ካልእቱ ፡ ወሰምዐ ፡ ኮኑ ፡ ላዕሌሁ ፡ ከመ ፡ ይትከላእ ፡ እምከዊነ ፡ ሰምዖሙ ፡ ወከመ ፡ ይትመከነይ ፡ ከመ ፡ እሙንቱ ፡ ጸላእቱ ። ወዘይመስሎ ፡ ለዝንቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ዳእሙ ፡ ለእመ ፡ ተዐውቀ ፡ ከመ ፡ በክልኢሆን ፡ ጊዜያት ፡ ናሁ ፡ ኮነት ፡ ማእከሌሁ ፡ ወማእከሌሆሙ ፡ ተፃርሮ ፡ ዘይትዌከፉ ፡ ወትሬስዮሙ ፡ ንቁፋነ ፡ ለእለ ፡ ሰምዐ ፡ ኮኑ ፡ እው ፡ ለእመ ፡ ተክህሎ ፡ ከመ ፡ ያጠይቅ ፡ እምኢአ ፡ ሰማዕት ፡ ከመ ፡ ነገሮሙ ፡ ሐሰት ፡ ውእቱ ።

፩ሺ፭፻፳፯ ሳድስ ፡ እመቦ ፡ ዘአምጽአ ፡ ሰማዕተ ፡ ፪ተ ፡ ጊዜያተ ፡ ወኢያምጽአ ፡ ካልእኒሆሙ ፡ እምድኅረ ፡ ተዐውቀ ፡ ሐሰቶሙ ፡ በቅድሜሁ ፡ ወንዋ፡ ይከውን ፡ እምቅድመ ፡ ተናግሮቶሙ ፡ ከመ ፡ ያብጽሕ ፡ ፬ተ ፡ ሰማዕተ ።

፩ሺ፭፻፳፰ ሳብዕ ፡ ወለኵሉ ፡ ሰከዩ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ያስተሐምም ፡ በጥያቄ ፡ ከመ ፡ ንዋዩ ፡ ሎቱ ፡ ኢተንሥአ ፡ በጽድቅ ፡ ወከመ ፡ ንዋይ ፡ ኢኮነ ፡ ለስደው ፡ እሳ ፡ ውእቱስ ፡ ለካልኣኒሆሙ ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይንበር ፡ ንዋይ ፡ ለዘሀሎ ፡ ውስተ ፡ እደሁ ፡ ወኢይከውኖ ፡ ለመኑሂ ፡ ከመ ፡ ያብጽሕ ፡ ሰማዕተ ፡ ከመ ፡ ዘሰከዩ ፡ ኮነ ፡ ውእቱ ፡ ዚአሁ ።

፩ሺ፭፻፳፱ ሳምን ፡ በእንተ ፡ ኅቢእ ፡ እምከዊነ ፡ ሰምዕ ፡ ለእመ ፡ ኀብአ ፡ ሰማዕት ፡ እምስምዖሙ ፡ በቅ

ስለ ፡ ዳኛ ።

ይጠቅሱ ፡ እንደሆነ ፡ በሚጠቅም ፡ ገንዘብ ፡ ስለ እርሱ ፡ ስለጠየቋቸው ፡ ነገር ፡ ይመልሱም ፡ እን ደሆነ ፡ የማይቀበሏትም ፡ የነገር ፡ ምልክት ፡ ምን ፡ እንደሆነች ፡ ዳኛው ፡ ይጠብቅ ።

፩ሺ፭፻፳፬ ፬ኛው ፡ ስለሚመረጡትና ፡ ስለሚመርጧ ቸው ፡ ይናገራል ። ጠሰ ፡ ፳፯ ። ምስክር ፡ ከሚ ሆኑት ፡ ወገን ፡ ሕፃናት ፡ እእምሮን ፡ ከፈለጓ ቸው ፡ ይፈትኗቸው ። ያልነበረው ፡ ሰው ፡ ምስክ ርነቱ ፡ የሚገባ ፡ ቢሆንም ፡ ሳይፈትኑት ፡ ምስክ ርነቱን ፡ አይቀበሉት ።

፩ሺ፭፻፳፭ መጅ ፡ ፭ ። ሊያነጹት ፡ የማይገባውን ፡ አታ ንጹት ። መማለጃ ፡ (ጉቦ) ፡ በመቀበል ፡ ክፉ ፡ የሆነውን ፡ ለሚያነጻው ፡ የእውነት ፡ ፍርድንም ከድኻው ፡ ለሚመልሳትና ፡ የሚገባውን ፡ ለሚ ከለክለው ፡ ወዮለት ፡ የሚል ፡ እነሆ ፡ ተጽፏል። (ኢሳ ፡ ፭ ፡ ፳-፳፫) ።

፩ሺ፭፻፳፮ ፭ኛ ። ጠሰ ፡ ፳፯ ። ከጠላቶቹ ፡ ወገን ፡ ምስክ ር ፡ የመጣ ፡ ሰው ፡ ወደሌላዋም ፡ ነገር ፡ ደርሰው በእርሱ ፡ ላይ ፡ ምስክር ፡ ቢሆኑ ፡ ከምስክርነታ ቸው ፡ ሁኔታ ፡ ይከለክል ፡ ዘንድ ፡ እነርሱም ፡ ጠላቶቹ ፡ እንደሆኑና ፡ ይህንም ፡ በመሰለው ፡ ያመካኝ ፡ ዘንድ ፡ አይገባውም ። በሁለቱ ፡ ጊዜ ያቶች ፡ በእርሱና ፡ በእነርሱ ፡ መካከል ፡ ምስክር የሆኑትን ፡ ሰዎች ፡ የተነቀፉ ፡ የምታደርጋቸው፡ የሚያውቋት ፡ ጥል ፡ እንዳለች ፡ ቢታወቅ ፡ ወይም ፡ ነገራቸው ፡ ሐሰት ፡ እንደሆነ ፡ ምስክ ሮችን ፡ እምጥቶ ፡ ሊያስረዳ ፡ ቢቻለው ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፩ሺ፭፻፳፯ ስድስተኛ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ምስክሮችን ፡ ያመጣ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ሐሰተኛነታቸው ፡ በፊቱ ፡ ከታወቀ ፡ በኋላ ፡ ሌሎቹን ፡ ባያመጣ ፡ እነርሱ ፡ ከመናገራቸው ፡ አስቀድሞ ፡ አራት ፡ ምስክሮች ፡ ሊያቀርብ ፡ እነሆ ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ፭፻፳፰ ሰባተኛ ፡ ከሳሽ ፡ ለሆነ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ገን ዘቡ ፡ በእውነት ፡ እንዳልሄደበት ፡ ገንዘብም ፡ ለባላጋራው ፡ እንዳልሆነ ፡ በማረጋገጥ ፡ ሊተጋ፡ ይገባዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ለሌሎቻቸው ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ገንዘብ ፡ በእጁ ፡ ላለ ፡ ሰው ፡ ሊኖር ፡ ይገባል ። ለማንም ፡ ሰው ፡ የከሰሱበት ፡ ገንዘብ ፡ የእርሱ ፡ እንደሆነ ፡ ምስክር ፡ ሊያቀር ብ ፡ አይገባውም ።

፩ሺ፭፻፳፱ ስምንተኛ ፡ ምስክር ፡ ከመሆን ፡ ስለመሠ ለስ ፡ ይናገራል ። ምስክሮች ፡ ከፍርድ ፡ አስቀድ

አንቀጽ ፡ ፵፬ ።

ድመ ፡ ፈታሒ ፡ እምቅድመ ፡ ፍትሕ ፡ ይፀራዕ ፡ ፍትሕ ፡ ወለእመ ፡ ገብአ ፡ እምድኅሬሁ ፡ ኢይሠዐር ፡ ፍትሕ ፡ ወይደልዎሙ ፡ ዕዳ ፡ በዕሪና ፡ ለዘአጥፍእዎ ፡ በስምዖሙ ። ወለእመ ፡ ገብአ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ይደልዎ ፡ መንፈቀ ፡ ዕዳ ፡ ወለእመ ፡ ኮኑ ፡ ፫ቱ ፡ አው ፡ ዘይበዝኅ ፡ ወገብአ ፡ ተውሳክ ፡ ላዕለ ፡ ፪ቱ ፡ ወኢይደልዎሙ ፡ ዕዳ ፡ በምንትኒ ፡ እስመ ፡ ኢጠፍአ ፡ ምንትኒ ፡ እምንዋይ ፡ በግብአተ ፡ ዚአሆሙ ። ወለእመኒ ፡ ተመይጡ ፡ ፪ቱ ፡ አው ፡ ዘይበዝኅ ፡ እስከ ፡ ኢይተርፍ ፡ ዘእንበለ ፡ ፩ዱ ፡ ይደልዎሙ ፡ ለእለ ፡ ገብኡ ፡ ዕዳ ፡ መንፈቀ ፡ ንዋይ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ መጠኑ ፡ ለዘአጥፍእዎ ።

ስለ ፡ ነገሥታት ።

መጡ ፡ በዳኛው ፡ ፊት ፡ ከምስክርነታቸው ፡ ቢመለሱ ፡ ፍርድ ፡ ይቀራል ። ከተፈረደ ፡ በኋላ፡ ቢመለሱ ፡ ግን ፡ ፍርድ ፡ አይሻርም ። በምስክርነታቸው ፡ ላጠፉት ፡ በትክክል ፡ ዕዳ ፡ ይገባቸዋል ። ከእነርሱም ፡ አንዱ ፡ ቢመለስ ፡ የዕዳ ፡ እኩሌታ ፡ ይገባዋል ። ፫ ፡ ወይም ፡ የሚበዙ ፡ ቢሆኑ ፡ ጭማሪ ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ ተመለሰ ። ዕዳም ፡ በምንም ፡ አይገባቸውም ። በእነርሱ ፡ መመለስ ፡ ከገንዘቡ ፡ ምንም ፡ አልጠፋምና ፡ ሁለቱ ፡ ወይም ፡ የሚበዙት ፡ አንድ ፡ እስከማይቀር ፡ ድረስ ፡ ቢመለሱ ፡ ለተመለሱት ፡ ሰዎች ፡ የገንዘቡ ፡ እኩሌታ ፡ ዕዳ ፡ ይገባቸዋል ። ላጠፉት ፡ ገንዘብ ፡ ልኩ ፡ ይህ ፡ ነውና ።

## አንቀጽ ፡ ፵ወ፬ቱ ፡

### በእንተ ፡ ነገሥት ።

፩ሺ፰፻፴ ወውእቱ ፡ ፰ቱ ፡ ምዕራፍ ። ምዕራፍ ፡ ቀዳማዊ፡ ትሔ ፡ ወይኩን ፡ ንጉሥ ፡ ዘትሠይሞ ፡ እምአኀዊከ ፡ ወኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ትሚም ፡ ላዕሌከ ፡ ብእሴ ፡ ነኪረ ፡ ዘኢማእምን ፡ ከመ ፡ ኢያብዝኅ፡ አፍራሰ ፡ ወኢ ፡ አንስተ ፡ ወኢ ፡ ወርቀ ፡ ወኢ ፡ ብሩረ ።

፩ሺ፰፻፴፩ ወእመ ፡ ይነብር ፡ ዲበ ፡ መንበረ ፡ መንግሥቱ ፡ ይጽሐፉ ፡ መጽሐፈ ፡ እምላካዌ ፡ እምካህናት ፡ ከመ ፡ የሀሉ ፡ ኀቤሁ ፡ ያንብብ ፡ ኪያሁ ፡ በኵሉ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ከመ ፡ ይትመሀር ፡ ፈሪሀ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጣሪሁ ፡ ወይዕቀብ ፡ ትእዛዛቲሁ ፡ ወይግበር ፡ ኪያሃ ፡ ከመ ፡ ኢይትዐበይ ፡ ልቡ ፡ ላዕለ ፡ አኀዊሁ ፡ ወኢይትገኀሥ ፡ እምሥርዓተ ፡ ሕግ ፡ ኢ ፡ ለየማን ፡ ወኢ ፡ ለፀጋም ፡ ከመ ፡ ትኑኅ ፡ መዋዕሊሁ ፡ በውስተ ፡ ንግሡ ፡ ሎቱኒ ፡ ወለደቂቁ ፡ ወይኩኑ ፡ አሚኖቱ ፡ ፍጹመ ፡ በእግዚአብሔር ።

፩ሺ፰፻፴፪ ዕብ ፡ ፲፩ ፡ "በተአምኖ ፡ ወድቀ ፡ አረፍቱሃ ፡ ለኢያሪኮ ፡ አመ ፡ ዖድዋ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ለሱባዔ ፡ ዕለተ ፡ ወበተአምኖ ፡ ጌዴዎን ፡ ወባርቅ ፡ ወሶምሶን ፡ ወዮፍታሔ ፡ ወዳዊት ፡ ሞኡ ፡ ነገሥተ ፡ ወገብሩ ፡ ጽድቀ ፡ ወረከቡ ፡ ዘተሰፈዉ ፡ ወኮኑ ፡ መዋዕያነ ፡ በውስተ ፡ ጸብአ ፡ ወሞዑ ፡ ተዓይነ ፡ ፀር" ።

## አንቀጽ ፡ ፵፬ ።

### ስለ ፡ ነገሥት ፡ ይናገራል ።

፩ሺ፰፻፴ እርሱም ፡ ፰ ፡ ምዕራፍ ፡ ነው ፡ ፩ኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ትሄ ። የምትሾመው ፡ ንጉሥ ፡ ከወንድሞችህ ፡ ወገን ፡ ይሁን ። ያላመነ ፡ ባዕድ ፡ ሰውን ፡ በላይህ ፡ ልትሾም ፡ አይገባም ። ፈረሶችን ፡ ሴቶችንም ፡ ወርቅና ፡ ብርንም ፡ እንዳያበዛ ።

፩ሺ፰፻፴፩ በመንግሥቱ ፡ ዙፋን ፡ በተቀመጠ ፡ ጊዜ ፡ ከካህናት ፡ ወገን ፡ እምላካዊ ፡ መጽሐፍን ፡ ይጻፉለት ። ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ባለ፡ ዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ እርሱን ፡ ያንብብ ። ፈጣሪውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍራትን ፡ ይማር ፡ ዘንድ ። ሕጉንም ፡ ይጠብቅ ፡ ዘንድ ። እርሱዋንም ፡ ይሥራ ። ልቡ ፡ በወንድሞቹ ፡ ላይ ፡ እንዳይታበይ ። ከሕግ ፡ ሥርዓትም ፡ ወደቀኝ ፡ ወይም ፡ ወደግራ ፡ ፈቀቅ ፡ አይበል ። ለእርሱና ፡ ለልጆቹ ፡ ዘመኑ ፡ በመንግሥቱ ፡ ይረዝም ፡ ዘንድ ። (ዘዳ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰ - ፳) ። በእግዚአብሔርም ፡ ማመኑ ፡ ፍጹም ፡ ይሁን ።

፩ሺ፰፻፴፪ ዕብ ፡ ፲፩ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በሃይማኖት ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ በዞሩዋት ፡ ጊዜ ፡ የኢያሪኮ ፡ ቅጽር ፡ ተናደ ። ጌዴዎንና ፡ ባርቅ ፡ ሶምሶንና ፡ ዮፍታሔም ፡ ዳዊትም ፡ በሃይማኖት ፡ ነገሥትን ፡ ድል ፡ አደረጉ ። እውነትንም ፡ ሠሩ ። ተስፋ ፡ ያደረጉትንም ፡ አገኙ ። በሰልፍም ፡ ውስጥ ፡ ድል ፡ አድራጊዎች ፡ ሆኑ ። የጠላትንም ፡ ጦር ፡ ድል ፡ ነሡ ። (ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፴ - ፴፭) ።

አንቀጽ ፡ ፶፬ ።

፩ሺ፫፻፴፫ ረስጣ ፡ ፶ወ፬፡ ፡ ወንጉሥኒ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ መናፍቀ ፡ ኢኮነ ፡ ዓዲሁ ፡ ንጉሠ ፡ እምይእዜ ፡ አላ ፡ አላዊ ፡ ውእቱ ።

፩ሺ፫፻፴፬ ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ በወንጌሉ ፡ ‘‘ሀቡ ፡ ዘንጉሥ ፡ ለንጉሥ ፡ ወዘእግዚአብሔር ፡ ለእግዚአብሔር ’’ ። ወይቤ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ በመልእክቱ ፡ ለሰብአ ፡ ሮሜ ፡ ነፍሉ ፡ ሰብእ ፡ እምኔክሙ ፡ ለይግነይ ፡ ለሥልጣነ ፡ መኰንንን ፡ በቢይ ፡ እስመ ፡ ኢይሠየም ፡ መኰንንን ፡ ዘእንበለ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ። ወለኵሉ ፡ መኳንንት ፡ ነተሎሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሢሞሙ፡ ወአሠልጠኖሙ ፡ ወዘተቃወሞ ፡ ለመኰንን ፡ ወበለዎ ፡ በለወ ፡ ትእዛዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጠሪሁ ፡ ወእለሂ ፡ ይትቃወምዎሙ ፡ ይትኴነኑ ። ወሊቃናትሰ ፡ ወመኳንንት ፡ ኢኮኑ ፡ ግሩማነ ፡ ለእለ ፡ ይገብሩ ፡ ሠናየ ፡ አላ ፡ ለእለ ፡ ይገብሩ ፡ እኩየ ። ወእመሰ ፡ ፈቀድከ ፡ አ ፡ ብእሲ ፡ ከመ ፡ ኢትፍርሆ ፡ ለመኰንን ፡ ግበር ፡ ሠናየ ፡ ከመ ፡ ትትወደስ ፡ በኀቤሁ ፡ እስመ ፡ ላእከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ወገብረ ፡ ዘእሁ ፡ ዘይጼውዐከ ፡ ኀበ ፡ ኂሩት ፡ ወሠናይት ። ወእመሰ ፡ ገበርከ ፡ እኩየ ፡ ፍርሆ ፡ ለመኰንን ፡ ውተበቀብ ፡ ኪያሁ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ኢቀንተ ፡ መጥባሕተ ፡ በከንቱ ፡ ወባሕቱ ፡ ላዕከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ወይትበቀል ፡ በመዓት ፡ እምእለ ፡ ይገብሩ ፡ እኩየተ ። ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ መፍትው ፡ ከመ ፡ ንግነይ ፡ ሎቱ ፡ አኮ ፡ በእንተ ፡ ፍርሃተ ፡ መዓቱ ፡ ባሕቲቱ ፡ አላ ፡ በእንተ ፡ ሕሊናቲነ ። ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ንወስድ ፡ ሎቱ ፡ ጸባሕተ ፡ እስመ ፡ እለ ፡ ይሠየሙ ፡ ለአስተጻንዖ ፡ ግብረት ፡ ላእካነ ፡ እግዚአብሔር ፡ እሙንቱ ፡ ወገባርያነ ፡ ፈቃደ ፡ ዚአሁ ። ሀቡ ፡ ለኵሉ ፡ ብእሲ ፡ ዘይደልዎ ፡ ወለዘሂ ፡ ይደልዎ ፡ ጸባሕት ፡ ጸባሕቶ ፡ ወለዘሂ ፡ ይደልዎ ፡ ፍርሃት ፡ ፍርሆ ፡ ወለዘሂ ፡ ይደልዎ ፡ ክብር ፡ ክብረ ፡ አክብሩ ። ወለዘሂ ፡ ይደልዎ ፡ ዓሥራት ፡ ዓሥራተ ፡ ዓሥሩ ።

ስለ ፡ ነገሥታት ።

፩ሺ፫፻፴፫ ረስጣ ፡ ፶፬ ። ንጉሥ ፡ መናፍቅ ፡ ቢሆን ፡ ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ ገና ፡ ንጉሥ ፡ አልሆነም ፡ ሀላዊ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፩ሺ፫፻፴፬ ሁለተኛ ፡ ምዕራፍ ። ጌታ ፡ በወንጌል ፡ የንጉሥን ፡ ለንጉሥ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስጡ ፡ አለ ። (ማቴ ፡ ፳፪ ፡ ፳፩) ። ሐዋርያ ፡ ጳውሎስም ፡ ለሮም ፡ ሰዎች ፡ በላከው ፡ መልእክት ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ከእናንተ ፡ ሰዉ ፡ ሁሉ ፡ ሊታላቁ ፡ መኰንንን ፡ ሥልጣን ፡ ይገዛ ። ገዥ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አይሾምምና ። እሊህንም ፡ መኳንንቶች ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሾሚቸዋል ። አሠልጥኖዋቸዋልም ። ዳኛውንም ፡ የተቃወመውና ፡ የወነጀ ሰው ፡ የፈጣሪውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ፡ ወነጀለ ። እነርሱን ፡ የሚቃወሟቸውም ፡ ይቀጣሉ ። ሊቃናትና ፡ መኳንንትስ ፡ ክፉ ፡ ለሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መልካም ፡ ለሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ግሩማን ፡ አይደሉም ። ሰው ፡ ሆይ ፡ ገዥን ፡ እንዳትፈራው ፡ ከወደድክስ ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ እንድትመሰገን ፡ መልካም ፡ አድርግ ። የእግዚአብሔር ፡ መላክተኛ ፡ እንተን ፡ ወደፍጹም ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ የሚጠራህ ፡ የርሱ ፡ ባሪያ ፡ ነውና ። ክፉ ፡ ሥራ ፡ ብትሠራ ፡ ግን ፡ ዳኛውን ፡ ፍራው ። ከእርሱም ፡ ተጠበቅ ። እርሱ ፡ ሰይፍን ፡ በከንቱ ፡ አልታጠቀምና ። እርሱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መላክተኛ ፡ ነው ፡ እንጂ ። ክፉ ፡ የሚሠሩትን ፡ ሰዎች ፡ በመዓት ፡ ይበቀላል ። ስለዚህ ፡ ልንገዛለት ፡ ይገባል ። መዓቱን ፡ ብቻ ፡ ስለመፍራት ፡ አይደለም ። በሐሳባችንም ፡ ነው ፡ እንጂ ። ስለዚህ ፡ ግብር ፡ እንወስድለታለን ። እነርሱ ፡ ሥራዎችን ፡ ለማስፈጸም ፡ የተሾሙ ፡ ፈቃዱንም ፡ የሚፈጽሙ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገልጋዮች ፡ ናቸውና ። ለሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚገባውን ፡ ስጡ ። ግብር ፡ ለሚገባውም ፡ ገብሩ ። መፈራት ፡ የሚገባውንም ፡ መፍራትን ፡ ፍሩ ። ክብር ፡ የሚገባውንም ክብርን ፡ አክብሩ ። ዐሥራት ፡ ለሚገባውም ፡ ዓሥራትን ፡ ስጡ ። (ሮሜ ፡ ፲፫ ፡ ፩ - ፰) ።

፩ሺ፫፻፴፭ ወይቤ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ በትርጓሜሁ ፡ ዘንቱ ፡ ክፍል ፡ ናሁ ፡ አመረ ፡ ሐዋርያ ፡ በውስተ ፡ ካልእት ፡ መልእክታቲሁ ፡ ወእዘዞሙ ፡ ለሥዩማን ፡ ሥነ ፡ ተአዝዞ ፡ ለሊቃውንት ፡ በከመ ፡ ይትኤዘዙ ፡ አግብርት ፡ ለእጓእዝት ። ወዘንቱ ፡

፩ሺ፫፻፴፭ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅም ፡ ይህን ፡ ክፍል ፡ በተረጐመበት ፡ እንዲህ ፡ አለ ። እነሆ ፡ ሐዋርያ ፡ በሌሎች ፡ መልእክቶቹ ፡ አመለከተ ። ሹማምት ፡ ለሊቃውንት ፡ በጎ ፡ መታዘዝን ፡ እንዲታዘዙ ፡ አዘዛቸው ። ባሮች ፡ ለጌቶች ፡ እንደሚታ

አንቀጽ ፡ ፵፱ ።

ግብረ ፡ እንዘ ፡ ያርኢ ፡ ከመ ፡ እግዚእን ፡ በትእዛ
ዛቲሁ ፡ ኢያግኅሦሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ሐረታት ፡
እላ ፡ አስተጸንዖሙ ፡ ባቲ ። ወብሂሎቱኒ ፡ ኵሉ፡
ነፍስ ፡ ዝኒ ፡ ይደልዎሙ ፡ ለኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ይት
መሰሉ ፡ ባቲ ። "ወብሂሎቱኒ ፡ ኢይሠየም ፡
መኰንን ፡ ዘእንበለ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር"
ዝ ፡ ብሂል ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ረሰየ ፡
ከመ ፡ ይኩን ፡ ድልወ ፡ ከዊነ ፡ ሢመት ፡ ለሊ
ቃናት ፡ ወመኳንንት ፡ ከመ ፡ ይሠእርዎ ፡
ዓለም ፡ በሠናይ ።

፩ሺ.፭፻፵፮ ወበእንተዝ ፡ ሠርዐ ፡ መኳንንተ ፡ በእንተ ፡
ዘኮነ ፡ ስሪና ፡ ዘተኀድሎ ፡ ይወልድ ፡ ጸብእ ፡
ብዙኀ ፡ ወሠርዐ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጥበቢሁ ፡
ሢመታተ ፡ ብዙኀ ፡ ዘከመ ፡ ብእሲ ፡ ወብእሲት
ወእብኒ ፡ ምስለ ፡ ወልዱ ፡ ወእረጋዊ ፡ ምስለ ፡
ወሬዛ ፡ ወገብርኒ ፡ ምስለ ፡ እግዓዚ ፡ ወመምህ
ርኒ ፡ ምስለ ፡ ረድኡ ፡ ወፈድፋደሰ ፡ ሊቅ ፡
ምስለ ፡ ዘይሠየም ፡ እምታሕቴሁ ። ወከማሁ ፡
ካዕበ ፡ ገብረ ፡ ውስተ ፡ ሥጋ ፡ ዘየንተግ ፡ ሊቀ
ወካልእ ፡ ሥዩመ ፡ በታሕቴሁ ፡ ወከማሁ ፡
ካዕበ ፡ ገብረ ፡ ከመዝ ፡ በብዙኃን ፡ እምተረፈ ፡
እንስሳ ፡ ዘከመ ፡ ንህብ ፡ ወሬዛ ፡ ወኰራኪ ፡
ወቆራት ፡ ወእንስርት ፡ ወእልሕምት ፡ ገዳም ፡
ወዘመደ ፡ ዓሣት ፡ ዘዘዚአሆሙ ።

፩ሺ.፭፻፵፯ ውኅበ ፡ ኢሀሎ ፡ ሢመት ፡ ይከውን ፡ ህከክ ፡
ወተኀጥአ ፡ ሥርዓት ። ወብሂሎቱኒ ፡ እስመ ፡
ላእከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ይጼውዐከ ፡
ኀበ ፡ ኄራት ፡ ወሠናያት ፡ ዝብሂል ፡ ያስተምህረ ፡
ተእዝዞተከ ፡ ለእግዚአብሔር ። ወከንኑሁሰ ፡
ለዐማፅያን ፡ እግዚአብሔር ፡ ለቀታልያን ፡ ወለ
ዘማውያን ፡ ለሰረቅት ፡ ወለገባርያን ፡ እከይ ።
ወእሠንዮቱሰ ፡ ለተእዛዝያን ፡ እለ ፡ ይትኤዘዙ ፡
ሎቱ ፡ ለልዑል ፡ ይትለዐል ፡ ስሙ ፡ ለመናንያን
ዓለም ፡ ወትሩፋን ፡ ምግባር ፡ ወጻድቃን ።

፩ሺ.፭፻፵፰ ወበእንተ ፡ በቀዓትነ ፡ እምኀቤሁ ፡ መን
ፈሳዊ ፡ ወሥጋዊ ፡ ነሀበ ፡ ሎቱ ፡ ጸባሕተ ፡ ወጋ
ዳ ፡ በእንተ ፡ ፍዳ ፡ በበይነ ፡ ዝንቱ ፡ ወበዘከመ ፡
ዝንቱ ፡ ግብር ፡ ይከውን ፡ ተሰናእዎ ፡ በእንተ ፡
ተዋፃ ፡ ለዘይፈትዱ ፡ ኀቢሁ ፡ መኳንንተ ፡
ሕግ ፡ ወውእቶሙ ፡ እስመ ፡ የኀድጉ ፡ እሙንቱ።

ስለ ፡ ነገሥታት

ዘዙ ። ጌታችን ፡ በትእዛዞቹ ፡ እካሄዶችን ፡
ሁሉ ፡ በእርሱዋ ፡ አጸናቸው ፡ እንጂ ፡ እንዳሳሬ
ቃቸው ፡ ሲያሳዩ ፡ ይህን ፡ አደረገ ። "ነፍስ ፡
ሁሉ ፡ ማለቱም" ፡ ለሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በእርሱዋ ፡
ሊመስሉ ፡ ይገባቸዋል ። "ሹም ፡ ከእግዚአብሔ
ር ፡ ዘንድ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አይሾምም" ፡ ማለ
ቱም ፡ እንዲህ ፡ ማለት ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡
የሹመትን ፡ እኳኋን ፡ ለሊቃውንትና ፡ ለመኳ
ንንት ፡ የተገባ ፡ እንዲሆን ፡ አድርጓልና ። ዓለም
በመልካም ፡ ይከናወን ፡ ዘንድ ።

፩ሺ.፭፻፵፮ ስለዚህ ፡ መኳንንትን ፡ ሾመ ። በኀይል ፡ መተ
ካከል ፡ ብዙ ፡ መጣላትን ፡ የሚወልድ ፡ ስለሆነ፡
እግዚአብሔር ፡ በጥበቡ ፡ ብዙ ፡ ሹመቶችን ፡
ሠራ ። እንደ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ እንደ ፡ እባትና ፡
ልጅ ፡ እንደ ፡ ሽማግሌና ፡ ጎልማሳ ፡ እንደ ፡ ባሪ
ያና ፡ ጌታው ፡ እንደ ፡ መምህርና ፡ ተማሪው፡ይ
ልቁንም ፡ ከበታቹ ፡ እንደተሾመ ፡ ሊቅ ፡ ያለ
ነው ። ዳግመኛም ፡ እንደዚሁ ፡ ስለዚህ ፡ ፊንታ፡
በሥጋ ፡ አለቃ ፡ አደረገ ። ሌላውንም ፡ ሹም ፡ ከ
በታቹ ፡ ዳግመኛም ፡ እንደዚሁ ፡ ከእንስሳት ፡
ወገን ፡ በብዙዎቹም ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ። ይኸውም
እንደንብ ፡ እንደ ፡ ሽመላ ፡ አሞራ ፡ እንደ ፡
ምስጥ ፡ እንደ ፡ ቁራዎች ፡ እንደ ፡ አሞሮች ፡ እንደ ፡
ዱር ፡ ከብቶችም ፡ (እንደ ፡ ጎሾች) ፡ እንደ ፡
ዐሣዎችም ፡ ወገኖች ፡ በየወገናቸው ፡ ናቸው ።

፩ሺ.፭፻፵፯ ሹም ፡ ከሌለ ፡ ዘንድ ፡ ክርክር ፡ የሥርዓትም፡
መታጣት ፡ ይሆናል ። "የእግዚአብሔር ፡ መላ
ክተኛ ፡ ነውና ፡ ወደፍጹም ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡
ይጠራሃል" ፡ ማለቱም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መታ
ዘዝህን ፡ ያሳምርልሃል ፡ ማለቱ ፡ ነው ። ቅጣ
ቱም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ለሚያምፁ ፡ ለነፍስ ፡
ገዳዮችና ፡ ለሴሰኞች ፡ ለሌቦችና ፡ ክፉን ፡ ለሚ
ያደርጉ ፡ ነው ። በጎ ፡ ማድረጉም ፡ ስሙ ፡ ከፍ ፡
ከፍ ፡ ይበልና ፡ ለልዑል ፡ ለሚታዘዙና ፡ ዓለ
ምን ፡ ለናቁ ፡ ሥራቸውም ፡ ለበዛ ፡ ለጻድቃን ፡
ነው ።

፩ሺ.፭፻፵፰ ከእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ስለሚሆን ፡ ሥጋዊና ፡ መን
ፈሳዊ ፡ ጥቅማችንም ፡ ግብርንና ፡ እጅ ፡ መን
ሻን ፡ ለእርሱ ፡ እንሰጠው ። በዚህ ፡ ስለብድራት
በእንደዚህም ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ የሕግ ፡ መኳንን
ት ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ለሚሹት ፡ ስለመጽናት ፡
መስማማት ፡ ይሆናል ። እነርሱ ፡ የራሳቸውን ፡

ጸሕቀ ፡ ዘእዘሙ ፡ ወይጸሕቁ ፡ ለዘቀኑዔቶ ፡ ዘተሉ ።

፩ሺ፩፻፵፱ ወኢትበሉ ፡ እስመ ፡ እንሌ ፡ አሕሠመ ፡ ሥር
ዓተ ፡ እላ ፡ ርእዩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ወኢከዊነ ፡
ሰላም ፡ ምስለ ፡ ኢቀዊመ ፡ ሢመት ፡ ወብዝኀ ፡
ሁከት ፡ ወቅብጸተ ፡ ሰላም ፡ ዘይወስድ ፡ ኀበ ፡
ትብጸተ ፡ ሰዶሚ ፡ ወሀልዎ ፡ በእንተ ፡ ቅብጸተ ፡
ሢመት ። እስመ ፡ አንትሙ ፡ ትሬእዩ ፡ ጥበ
ቢሁ ፡ ለሠራዔ ፡ ሕግ ፡ ዘሠርዖሙ ፡ ለግብራት ፡
ከዊኖ ፡ ቀዳማዊ ፡ በተዋሕዶቱ ። ወለእመ ፡
ትቤ ፡ ከመ ፡ እንተ ፡ በሃይማኖት ፡ ወበምግባር ፡
ትኄይስ ፡ እምኔሁ ፡ እእምር ፡ ከመ ፡ ጊዜከ ፡
ኢኮነ ፡ ውእቱ ፡ ጊዜ ፡ እስመ ፡ እንተ ፡ ይእዜ ፡
ፈላሲ ፡ እንተ ፡ ወድኩም ፡ ወናሁ ፡ ይመጽእ ፡
ጊዜከ ፡ ወውእቱ ፡ ኢተዐውቀ ፡ ዓዲሁ ፡ እስመ
እንተ ፡ ትኄይስ ፡ እምኔሁ ፡ ወዛቲሰ ፡ ዓፀድ ፡
ኢኮነት ፡ ዓፀደ ፡ ሰዔት ።

ስለ ፡ ነገሥታት ።

ግዳጅ ፡ ትተው ፡ ለሁሉ ፡ ጥቅም ፡ ይተጋሉና ።

፩ሺ፩፻፵፱ እገሌ ፡ ሥርዓት ፡ አጥፍቷል ፡ እኮ ፡ አት
በሉ ። የሥርዓትን ፡ መበጀት ፡ ሹመት ፡ ካል
ጸና ፡ ሰላም ፡ አለመሆኑን ፡ ሁከት ፡ መብዛ
ቱን ፡ እድሜን ፡ ተስፋ ፡ ወደመቍረጥ ፡ የሚያ
ደርስ ፡ ለሰላም ፡ ተስፋ ፡ መቍረጥን ፡ ለሹመት፡
ተስፋ ፡ ቆርጦ ፡ መኖርን ፡ እዩ ፡ እንጂ ። በአንድ
ነቱ ፡ ጀማሪ ፡ ሁኖ ፡ ግብራትን ፡ የሠራቸው ፡
የሠራዔ ፡ ሕግ ፡ ጥበቡን ፡ እናንተ ፡ ታያላች
ሁና ። አንተ ፡ በሃይማኖትና ፡ በምግባር ፡ ከእ
ርሱ ፡ እንደምትበልጥ ፡ ብትናገር ፡ ይህ ፡ ጊዜ ፡
ያንተ ፡ ጊዜ ፡ እንዳልሆነ ፡ እወቅ ። አንተ ፡ ዛሬ ፡
መጻተኛ ፡ ደካማም ፡ ነህና ። እነሆ ፡ ጊዜስ ፡ ይመ
ጣል ። እርሱም ፡ አንተ ፡ ከእርሱ ፡ ትበልጥ ፡
እንደሆነ ፡ ገና ፡ አልታወቀም ። ይህችም ፡ ቦታ፡
የዋጋ ፡ ቦታ ፡ አይደለችም ።

፩ሺ፩፻፶ ምስራፍ ፡ ፫ቱ ። መኑ ፡ ፴ወ፯ቱ ፡ ወያከብር ፡
መዓርጋተ ፡ ካህናት ፡ ከመ ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡
ንጉሥ ፡ ኅሩይ ፡ ወምእመን ፡ ወጻድቅ ፡ ወእለ ፡
እምድኅሬሁ ፡ ወያስተዋፅእ ፡ እንከ ፡ ላዕሌሆሙ
ለኵሎሙ ፡ እምነ ፡ ጸጋሁ ፡ ለለ፩ዱ ፡ ፩ዱ ፡
በከመ ፡ መጠነ ፡ መዓርጊሁ ፡ ወያቅድም ፡
ውሂበ ፡ ለኤጲስቆጶሳት ፡ ወእምዝ ፡ ለቀሳውስት
ወእምድኅሬሆሙ ፡ ለዲያቆናት ፡ ወእምዝ ፡
ለእለ ፡ ይቴሐትዎሙ ።

፩ሺ፩፻፶ ፫ኛ ፡ ምዕራፍ ። መክ ፡ ፴፪ ። የካህናትን ፡ መዓ
ርግ ፡ የተመረጠና ፡ የታመነ ፡ እውነተኛም ፡
እንደሆነ ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ ቆስጠንጢኖስ ፡
ከእርሱ ፡ በኋላም ፡ እንደነበሩ ፡ ነገሥታት ፡ ያከ
ብር ። ለሁሉም ፡ እያንዳንዱ ፡ እንደመዓርጉ ፡
መጠን ፡ ከሀብቱ ፡ ያወጣጣላቸው ። መስጠት
ንም ፡ ለኤጲስቆጶሳት ፡ ያስቀድም ። ከዚያም ፡
በኋላ ፡ ለቀሳውስት ፡ ቀጥሎም ፡ ለዲያቆናት ፡
ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ከእነርሱ ፡ በታች ፡ ላሉት ።

፩ሺ፩፻፶፩ ወያእትት ፡ እምኔሆሙ ፡ ጸባሕተ ፡ ወጋዳ ፡
ወግብረ ፡ መኳንንት ፡ ወያቅም ፡ ለእብያተ ፡
ክርስቲያናት ፡ ዘያሐይው ፡ ቦቱ ፡ ለዕቤራት ፡
ወለደካትም ፡ ወለምስኪናን ፡ ከመ ፡ ያስተብቍ
ዕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ያጽንዕ ፡ ሃይማ
ኖተ ፡ ርትዕተ ፡ በእሚነ ፡ ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡
ወከመ ፡ ይኑኅ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ለንጉሠ ፡ ክርስቲ
ያን ። ወይረሲ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መክፈልተ ፡
እምውስተ ፡ እምነ ፡ ወምሀርካ ፡ ከመ ፡ ዳዊት ፡
ንጉሥ ፡ ወካልእኒሁ ፡ እምነገሥት ፡ ጻድቃን ፡
ወኢያንሥእ ፡ እደዊሁ ፡ ኀበ ፡ ካህናተ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ወቅዱሳኒሁ ፡ ከመ ፡ ኢይርከቦ ፡ በከመ፡
ረከቦሙ ፡ ለነገሥት ፡ እኩያን ፡ እምእስራኤል ፡
ወካልእኒሆሙ ።

፩ሺ፩፻፶፩ ግብርንና ፡ እጅ ፡ መንሻን ፡ የመኳንንትንም ፡
ግብር ፡ ከእነርሱ ፡ ያርቅ ። ባልቴቶችና ፡
ደኃ ፡ አደጎች ፡ ጦም ፡ አዳሪዎችም ፡ የሚረዱበ
ትን ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይጕልት ። ሥሉስ ፡
ቅዱስን ፡ በማመን ፡ በቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ ያጸ
ናው ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይማልዱለት ፡
ዘንድ ። የክርስቲያን ፡ ንጉሥ ፡ ዘመኑም ፡ ይረ
ዝም ፡ ዘንድ ። ከደጋግ ፡ ነገሥታት ፡ ወገን ፡
እንደ ፡ ንጉሥ ፡ ዳዊት ፡ እንደሌሎችም ፡ ከእጅ ፡
መንሻውና ፡ ከምርኮውም ፡ ክፍሎ ፡ ለእግዚአብ
ሔር ፡ ያድርግ ። በእግዚአብሔር ፡ ካህናትና ፡
በቅዱሳኖቹ ፡ እጁን ፡ አያንሳ ። ከእስራኤል ፡
ወገን ፡ ከፉዎችን ፡ ነገሥታት ፡ ሌሎችንም ፡
እንዳገኛቸው ፡ እንዳያገኘው ። (፪ ፡ ዜና ፡ መዋ ፡
፴፫ ፡ ፲ - ፲፪) ።

፩ሺ፩፻፶፪ ትሔ ፡ ወእምከመ ፡ ቦእክሙ ፡ ኀበ ፡ ሀገር ፡
እንተ ፡ ይሁበክሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኪያሃ ፡

፩ሺ፩፻፶፪ ትሂ ። እግዚአብሔር ፡ እርሱዋን ፡ ወደሚሰ
ጣችሁ ፡ ሀገር ፡ ገብታችሁ ፡ በውስጡዋ ፡ በኖ

ወኀደርክሙ ፡ ውስቴታ ፡ ንሥኡ ፡ ቀዳምያተ ፡ ፍሬሃ ፡ ለምድር ፡ ወስዱ ፡ ኀበ ፡ መካን ፡ ዘኀረየ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀበ ፡ ካህን ፡ ዘተሠይመ ፡ በውእቱ ፡ ዘመን ። ወስግድ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክከ ፡ ወተፈሥሕ ፡ በኵሉ ፡ ሠናያት ፡ ዘጸገወከ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክከ ፡ አንተ ፡ ወቤትከ ፡ ወካህንኒ ፡ ወፈላሲ ፡ ዘሀሎ ፡ ውስተ ፡ ማኅደርከ ።

፩ሺ፭፻፵፫ ምስራፍ ፡ ፱ቱ ። ወመፍትው ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይፍታሕ ፡ ማእከለ ፡ መርዓቱ ፡ በርትዕ ፡ ወኢያድሉ ፡ ኢለነፍሱ ፡ ወኢ ፡ ለካልኡ ፡ ኢ ፡ ለወልዱ ፡ ወኢ ፡ ለአዝማዱ ፡ ኢ ፡ ለዓርኩ ፡ ወኢ ፡ ለነኪር ፡ በምንትኒ ፡ እምግጸ ፡ ዐመፃ ። ወናሁ ፡ ተጽሕፈ ፡ በእንተ ፡ ንጉሥ ፡ ዘይብል ፡ ክቡር ፡ ንጉሥ ፡ ፍትሐ ፡ ያፈቅር ፡ ወዐማፂሰ ፡ ይፈቅድ ፡ እክየ ፡ ወዐመፃ ፡ ለአኅጕሎተ ፡ ነፍሱ ። ወይቤ ፡ ሰሎሞን ፡ ጠቢብ ፡ አፈድፍዶ ፡ ርትዕ ፡ ወአድኅኖ ፡ ግፉዕ ፡ ይኄይስ ፡ እምቍርባን ፡ ወመሥዋዕት ።

ሪችሁ ፡ ጊዜ ፡ ከምድር ፡ ፍሬ ፡ ቀዳምያቱን ፡ ወስዳችሁ ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ እግዚአብሔር ፡ የመረጠው ፡ ካህን ፡ ወደተሾመበት ፡ ቦታ ፡ ውሰዱ ። በአምላክህ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ስገድ ። እግዚአብሔር ፡ በሰጠህ ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አንተና ፡ ቤተ ፡ ሰብህ ፡ ካህኑም ፡ በቤትህም ፡ ያለ ፡ መጻተኛ ፡ ደስ ፡ ይበልህ ። (ዘዳ ፡ ፳፮ ፡ ፩-፲፪) ።

፩ሺ፭፻፵፫ ፱ኛ ፡ ምዕራፍ ። በሕዝቦቹ ፡ መካከል ፡ በቅን ፡ ሊፈርድ ፡ ይገባዋል ። ለራሱ ፡ ለሌላውም ፡ ለልጁም ፡ ወይም ፡ ለዘመዱ ፡ ለወዳጁም ፡ ወይም ፡ ለባዕድ ፡ ቢሆን ፡ ከዓመፅ ፡ ወገን ፡ በምንም ፡ አያድላ ። እነሆ ፡ ስለንጉሥ ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ተጽፏል ። የከበረ ፡ ንጉሥ ፡ ፍርድን ፡ ይወድዳል ። ዓመፀኛ ፡ ንጉሥ ፡ ግን ፡ ነፍሱን ፡ ለማጥፋት ፡ ክፋትንና ፡ ዓመፅን ፡ ይወድዳል ። (መዝ ፡ ፺፰ ፡ ፬) ። ብልሁ ፡ ሰሎሞንም ፡ እውነትን ፡ ማብዛት ፡ የተበደለውንም ፡ ማዳን ፡ ከቍርባንና ፡ ከመሥዋዕት ፡ ይበልጣል ፡ አለ ። (ምሳ ፡ ፳፩ ፡ ፫) ።

፩ሺ፭፻፵፬ ወኢትንሣእ ፡ ንዋየ ፡ መኑሂ ፡ በኀይል ፡ ወኢትሣየጥ ፡ እምኔሁ ፡ በግብር ፡ ኢ ፡ በክሡት ፡ ወኢ ፡ በተመንግኖ ፡ ከመ ፡ ኢትሣቀይ ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዝዓለም ፡ ወበዘይመጽእ ፡ ዓለም ። በዓለምሰ ፡ በከመ ፡ ረከቦ ፡ ለአክዓብ ፡ ንጉሥ ፡ ወለኤልዛቤል ፡ ብእሲቱ ፡ ሶበ ፡ አበየ ፡ ናቡቴ ፡ ሠይጠ ፡ ዓፀደ ፡ ወይኑ ፡ ወተመንገት ፡ ኤልዛቤል ፡ ላዕለ ፡ ቀቲሎቱ ፡ ወነሥአ ፡ ለዓፀደ ፡ ወይኑ ፡ ወቀተሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአክዓብ ፡ ወአጥፍአ ፡ ዘርአ ፡ ዚአሁ ፡ ወእምድኅሬሁ ፡ ቀተላ ፡ ለኤልዛቤል ፡ ወበልዕዋ ፡ ከለባት ፡ ውስተ ፡ ውእቱ ፡ ዓፀደ ፡ ወይን ፡ ዘዘከርነ ። ወበደኃሪኒ ፡ ዓለም ፡ ይቤ ፡ ሐዋርያ ፡ "ከመ ፡ ዐማፅያን ፡ ወከሓድያን ፡ ኢይወርስዋ ፡ ለመንግሥተ ፡ እግዚአብሔር" ፡

፩ሺ፭፻፵፬ የማንንም ፡ ገንዘብ ፡ በኀይል ፡ አትውሰድ ። በግልጽም ፡ በተንኰልም ፡ ቢሆን ፡ በግድ ፡ ከእርሱ ፡ አትግዛ ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ በሚመጣውም ፡ ዓለም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ እንዳትሠቀይ ፡ በዓለምስ ፡ ንጉሥ ፡ አክዓብንና ፡ ሚስቱ ፡ ኤልዛቤልን ፡ እንዳገኛቸው ፡ ነው ። ናቡቴ ፡ የወይን ፡ ቦታውን ፡ አልሸጥም ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ኤልዛቤል ፡ እርሱን ፡ ለማስገደል ፡ ተተነኰለች ። የወይን ፡ ቦታውንም ፡ ወሰደበት ። እግዚአብሔርም ፡ አክዓብን ፡ ገደለው ። የእርሱንም ፡ ዘር ፡ አጠፋ ። ከእርሱም ፡ በኋላ ፡ ኤልዛቤልን ፡ ገደላት ። በተናገርነው ፡ የወይን ፡ ቦታም ፡ ውስጥ ፡ ውሾች ፡ በሉዋት ። (፪ ፡ ነገ ፡ ፱ ፡ ፴ - ፴፯ ። ፲ ፡ ፩ - ፳) ። በኋለኛውም ፡ ዓለም ፡ ዓመፀኞችና ፡ ከሀዲዎች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ እንዳይወርሱዋት ፡ ሐዋርያ ፡ ተናገረ ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፱) ።

፩ሺ፭፻፵፭ ወኢያሕሥም ፡ ላዕለ ፡ እጓለ ፡ ማውታ ፡ ወዕቤራት ፡ እስመ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ ትቤ ፡ ፲ወ፬ቱ ፡ ለእመ ፡ አሕሠምክሙ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ወጸርሑ ፡ ኀቤየ ፡ አነ ፡ እሰምዕ ፡ ገዓሮሙ ፡ ወእሠጠዎሙ ፡ ወእትመዐዕ ፡ በመዓትየ ፡ ወእቀትለክሙ ፡ በውስተ ፡ ጸብእ ፡ ወይከውና ፡ አንስቲያክሙ ፡ መበለታተ ፡ ወውሉድ

፩ሺ፭፻፵፭ በሙት ፡ ልጆችና ፡ በባልቴቶች ፡ ክፉ ፡ አያድርግ ። ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ብሏልና ። ትቤ ፡ ፲፬ ። ክፉ ፡ ብታደርጉባቸው ፡ ወደእኔም ፡ ቢጮሁ ፡ እኔ ፡ ጩኸታቸውን ፡ ሰምቼ ፡ አመልስላቸዋለሁ ። በመዓት ፡ ተቈጥቼ ፡ በሰልፍ ፡ ውስጥ ፡ አጠፋችኋለሁ ። ሚስቶቻችሁ ፡ ሴት ፡ አዳሪዎች ፡ ልጆቻችሁም ፡

አንቀጽ ፡ ፺፬ ።

ክሙ ፡ እንለ ፡ ማውታ ።

፩ሺ፰፻፺፮ ወይመግቦሙ ፡ ለአዕርክቲሁ ፡ ወለሐራሁ ፡ በአቅልሎ ፡ ወምሂክ ፡ ወይሑር ፡ በምክሮሙ ፡ ለአእሩግ ፡ ወለሊቃውንቲሆሙ ፡ ወኢይስማዕ በላዕሌሆሙ ፡ ምክረ ፡ ወራዙት ፡ እለ ፡ ተሐፅኑ ፡ ምስሌሁ ፡ ወኢያክብድ ፡ ቅኔሁ ፡ በላዕሌሆሙ ፡ ከዊኖ ፡ ግሡጸ ፡ በውእቱ ፡ ዘኮነ ፡ ላዕለ ፡ ወልዱ ፡ ለሰሎሞን ፡ አምኀበ ፡ አዕርክተ ፡ አቡሁ ።

፩ሺ፰፻፺፯ ወይግበር ፡ ሠናየ ፡ ለውሉደ ፡ ንጉሥ ፡ እለ ፡ ኮኑ ፡ እምቅድሜሁ ፡ በከመ ፡ ገብረ ፡ ዳዊት ፡ ለእዝርእተ ፡ ሳኦል ። ወዓዲ ፡ ይግበር ፡ ሠናየ ፡ ለላእካነ ፡ ንጉሥ ፡ ወኢያሕሥም ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ወይኩኖ ፡ ተግሣጸ ፡ ዘረከቦ ፡ ለንጉሠ ፡ እሞን ፡ ወወሀቦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዳዊት ፡ መዊአ ፡ በላዕሌሁ ፡ ሶበ ፡ አሕሠመ ፡ በላዕለ ፡ ላእካኒሁ ።

፩ሺ፰፻፺፰ ወእመኒ ፡ ኮነ ፡ አቡሁ ፡ ንጉሠ ፡ ይትዐቀብኬ ፡ ከመ ፡ ኢይስአሉ ፡ ኪያሁ ፡ ከመ ፡ ኢይቅትሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ በከመ ፡ ቀተሎ ፡ ለአቤሴሎም ፡ በውስተ ፡ ጸብእ ፡ እመ ፡ ሀለዎ ፡ ለአቡሁ ፡ ወፈቀደ ፡ ከመ ፡ ይንሣእ ፡ መንግሥቶ ።

፩ሺ፰፻፺፱ ትሔ ፡ ዘ፲ወ፫ቱ ፡ ወሶበ ፡ ተሐውር ፡ ኀበ ፡ ጸብእ ፡ ምስለ ፡ ሠራዊትከ ፡ ለጸቢአ ፡ ፀርከ ፡ ተዐቀብ ፡ እምኵሉ ፡ ግብር ፡ እኩይ ፡ ወእመቦ ፡ ዘኢኮነ ፡ ንጹሐ ፡ ለይፃእ ፡ አምትዕይንት ፡ ወይባእ ፡ በሳኒታሁ ፡ እምድኅረ ፡ ነጽሐ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ተዓይኒከ ፡ ቅዱሰ ፡ ከመ ፡ ኢይትረከብ ፡ ኀፍረት ፡ በማእከሌከ ፡ ወኢይትገኀሥ ፡ እምኔከ ።

፩ሺ፱፻ ዘ፲ወ፬ቱ ፡ ዘ፳ወ፩ቱ ፡ ለእመ ፡ ወፃእከ ፡ ለጸቢአ ፡ ፀርከ ፡ ወርኢከ ፡ አፍራሰ ፡ ወሠረገላተ ፡ ወሕዝበ ፡ ዘይበዝኁ ፡ እምኔከ ፡ ኢትፍራህ ፡ እምኔሆሙ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክከ ፡ ምስሌከ ። ወሶበ ፡ እኅዝከ ፡ ትትቃተል ፡ ይቅድም ፡ ካህን ፡ ነጊሮቶሙ ፡ ለሕዝብ ፡ ወይበሎሙ ፡ ናሁ ፡ አንትሙ ፡ ተሐውሩ ፡ ከመ ፡ ትትቃተልዎሙ ፡ ለፀርክሙ ፡ ኢይደንግፅክሙ ፡ ልብክሙ ፡ ወኢትፍርህዎሙ ፡ እምኔሆሙ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስሌክሙ ፡ ይጸብእ ፡ ጸላእተ

ስለ ፡ ነገሥታት ።

የሙት ፡ ልጆች ፡ ይሆናሉ ። (ዘፀ ፡ ፳፪ ፡ ፳፪ - ፳፭) ።

፩ሺ፰፻፺፮ ባለሟሎቹንና ፡ ጭፍሮቹን ፡ አገዛዝ ፡ በማቅለልና ፡ በመራራት ፡ ያስተዳድራቸው ። በሽማግሎችና ፡ በሊቃውንቶቻቸው ፡ ምክር ፡ ይኑር ። ከእነርሱ ፡ በላይ ፡ የአብሮ ፡ አደጎቹን ፡ ጎበዛዝት ፡ ምክር ፡ አይስማ ፤ ከአባቱ ፡ ባለሟሎች ፡ ምክር ፡ ቢወጣ ፡ በሰሎሞን ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ በሆነው ፡ በዚህ ፡ የተቀጣ ፡ ሁኖ ፡ አገዛዙን ፡ በላያቸው ፡ አያክብድ ። (፩ ፡ ነገ ፡ ፲፪ ፡ ፮ - ፲፮) ።

፩ሺ፰፻፺፯ ዳዊት ፡ ለሳኦል ፡ ዘሮች ፡ እንዳደረገው ፡ ሁሉ ከእርሱ ፡ አስቀድሞ ፡ ለነበረው ፡ ንጉሥ ፡ ልጆች መልካም ፡ ይሥራ ። (፪ ፡ ሳሙ ፡ ፱ ፡ ፩ - ፲፫) ። ዳግመኛም ፡ ለንጉሥ ፡ መልእክተኞች ፡ መልካም ፡ ይሥራ ። ክፉም ፡ አያድርግባቸው ። የአሞንን ፡ ንጉሥ ፡ ያገኘው ፡ መከራ ፡ ተግሣጽ ፡ ይሁነው ። በመላክተኞቹ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ በሠራ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ለዳዊት ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ድል ፡ መንሣትን ፡ ሰጠው ። (፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲ ፡ ፩ - ፲፯) ።

፩ሺ፰፻፺፰ አባቱ ፡ ንጉሥም ፡ ቢሆን ፡ እርሱን ፡ እንዳይከዳ ፡ ይጠበቅ ። አቤሴሎም ፡ አባቱን ፡ ክዶቶ ፡ መንግሥቱን ፡ ሊይዝ ፡ በወደደ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደገደለው ፡ እርሱንም ፡ እንዳይገድለው ። (፪ ፡ ሰሙ ፡ ፲፰ ፡ ፱ - ፲፯) ።

፩ሺ፰፻፺፱ ትሄ ፡ ፲፫ ። ጠላትህን ፡ ለመውጋት ፡ ከሠራዊትህ ፡ ጋር ፡ ወደሰልፍ ፡ በሄድክ ፡ ጊዜ ፡ ከክፉ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ተጠበቅ ። ንጹሕ ፡ ያልሆነ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ከከተማ ፡ ይውጣና ፡ ከነገ ፡ በኋላ ፡ በማግሥቱ ፡ ይግባ ። ሰልፍህ ፡ ቅዱስ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ። ነፍረትም ፡ በመካከልህ ፡ ተገኝቶ ፡ ከአንተ ፡ እንዳልርቅ ። (ዘዳ ፡ ፳፫ ፡ ፱ - ፲፭) ።

፩ሺ፱፻ ፲፬ ፡ ፳፩ ። ጠላትህን ፡ ለመውጋት ፡ ብትወጣ ፡ ፈረሶችንና ፡ ሠረገሎችን ፡ ከአንተ ፡ የሚበዙ ፡ ሠራዊትንም ፡ ብታይ ፡ ፈጣሪህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከአንተ ፡ ጋር ፡ ነውና ፡ ከእነርሱ ፡ የተነሣ ፡ አትፍራ ። ልትዋጋም ፡ በጀመርክ ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ ፡ ካህን ፡ ለሕዝቡ ፡ እነሆ ፡ እናንተ ፡ ጠላቶቻችሁን ፡ ልትወጉ ፡ ትሄዳላችሁ ። ልቡናችሁ ፡ አይሸበርባችሁ ። ከእነርሱም ፡ የተነሣ ፡ አትፍሩ ። እግዚአብሔር ፡ ከእናንተ ፡ ጋር ፡ ሁኖ ጠላቶቻችሁን ፡ ይወጋልና ። ከፊታቸውም ፡

ከሙ ፡ ወኢትትገኀሡ ፡ እምቅድመ ፡ ገጾሙ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክክሙ ፡ የሐውር ፡ ፍጽመ ፡ ለክሙሰ ፡ ያድኅንክሙ ፡ ወይቀትል ፡ በረከሙ ።

፩ሺ፰፻፶፩ ሥርዋጽ ፡ ወሀ ፡ ኀበ ፡ ተነግረ ፡ በውስተ ፡ ቀኖናት ፡ እለ ፡ ይሰመይ ፡ በስመ ፡ ነገሥት ፡ ወእምከመ ፡ ወፅኡ ፡ መሃይምናን ፡ ለጸቢእ ፡ ፀሮሙ ፡ ያቅሙ ፡ በቅድሜሆሙ ፡ መስቀለ ፡ ክርስቶስ ፡ ወይሰግዱ ፡ ሎቱ ፡ ወይጸርሑ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፵ተ ፡ ጊዜ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ኪርየ ፡ ላይሶን ። ወእምዝ ፡ ይንግር ፡ ዐዋዲ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ኢይምጻእ ፡ መኑሂ ፡ ኀበ ፡ ጸብእ ፡ በግብር ፡ ዘእንበለ ፡ ፈቃዱ ።

፩ሺ፰፻፶፪ ወእምከመ ፡ አሠለጠነከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ንብብ ፡ ሃይማኖተከ ፡ በቅድሜሆሙ ፡ ወእምከመ ፡ ረከብከ ፡ አማነ ፡ ጥዩቀ ፡ እሚነ ፡ ዚእሆሙ ፡ አኀዊከ ፡ እንከ ፡ እሙንቱ ፡ ወእመ ፡ አኮሰ ፡ ረሰዮሙ ፡ አግብርተ ፡ ዚአከ ፡ ለጸባሕት ፡ ወለተልእኮ ።

፩ሺ፰፻፶፫ ትሑ ፡ እመ ፡ በጻሕክሙ ፡ ኀበ ፡ ሀገር ፡ አው ፡ ኀበ ፡ ብሔር ፡ ከመ ፡ ትትቃተልዎሙ ፡ ለሰብእ ፡ ዚአሃ ፡ ጸውዕዎሙ ፡ ለከዊነ ፡ ዕርቅ ። ወለእመ ፡ ተወከፉክሙ ፡ ወአርኀዉ ፡ ለክሙ ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡ ውስቴታ ፡ እደው ፡ ይኩኑክሙ ፡ ከመ ፡ አግብርት ፡ ወየሀቡክሙ ፡ ጸባሕተ ።

፩ሺ፰፻፶፬ ወለእመ ፡ ኢተወከፉክሙ ፡ ለከዊነ ፡ ዕርቅ ፡ ወተጋደሉክሙ ፡ ወተጻብኡክሙ ፡ ጽብእዎሙ ፡ ወእፅፅቁ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክክሙ ፡ ያገብእ ፡ ለክሙ ።

፩ሺ፰፻፶፭ ወእመኒ ፡ ተማኅፀኑ ፡ ኀቤክሙ ፡ መሐርዎሙ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቤ ፡ ብፁዓን ፡ መሐርያን ፡ እስመ ፡ ሎሙኒ ፡ ይምሕርዎሙ ። ወእኩቶቱሰ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጺጋዊ ፡ ይደሉ ፡ በእንተ ፡ ዘመሐሮሙ ፡ ለአግብርቲሁ ። ወአርድእትኒ ፡ ሶበ ፡ ይቤልዎ ፡ ለእግዚእነ ፡ ንፈቅድ ፡ ትብል ፡ ለትረድ ፡ እሳት ፡ ወታውዕዮሙ ፡ በከመ ፡ ገብረ ፡ ኤልያስ ፡ ወከልአሙ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ኢተአምሩኑ ፡ ዘአይ ፡ መንፈስ ፡ አንትሙ ። እስመ ፡ በምሕረት ፡ ወበእፍቅሮተ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ ይትሜሰሎ ፡ ሰብእ ፡ ለፈጣሪሁ ፡ ወይትሌለይ ፡ መሲሓዊ ፡ እምካልእኒሁ ።

፩ሺ፰፻፶፮ ሥርዋጽ ፡ ትሑ ፡ ወለእመ ፡ ዐገትከ ፡ ለሀገር ፡

ፈቀቅ ፡ እትበሉ ። ፈጣሪያችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ፊታችሁን ፡ ይሄዳልና ። እናንተን ፡ ግን ፡ ያድናችኋል ። ጠላቶቻችሁንም ፡ ያጠፋቸዋል ፡ ብሎ ፡ ይንገራቸው ። (ዘዳ ፡ ፳ ፡ ፩ - ፬) ።

፩ሺ፰፻፶፩ ሥርዋጽ ። በነገሥታቱ ፡ ስም ፡ የተሠየሙ ፡ መጻሕፍት ፡ የተነገረም ፡ እለ ። ምእመናን ፡ ጠላታቸውን ፡ ለመውጋት ፡ ቢወጡ ፡ በፊታቸው ፡ የክርስቶስን ፡ መስቀል ፡ አቁመው ፡ ይሰግዱለት ። ኪርያላይሶን ፡ (እግዚኦ ፡ መሐረነ) ፡ እያሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ፵ ፡ ጊዜ ፡ ይጮኹ ። ከዚህ ፡ በኋላም ፡ አዋጅ ፡ ነጋሪ ፡ ማንም ፡ ያለፈቃዱ ፡ በግድ ፡ ወደሰልፍ ፡ አይምጣ ፡ እያለ ፡ አዋጅ ፡ ይንገር ።

፩ሺ፰፻፶፪ እግዚአብሔር ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ያሠለጠነህ ፡ ከሆነ ፡ ሃይማኖትህን ፡ በፊታቸው ፡ ተናገር ። የሃይማኖታቸውንም ፡ እርግጠኛነት ፡ በእውነት ፡ ካገኘህ ፡ እንግዲህ ፡ ወንድሞችህ ፡ ናቸው። ይህ ፡ ባይሆን ፡ ግን ፡ ለገባርነትና ፡ ለአገልግሎት ፡ ባሮችህ ፡ አድርጋቸው ።

፩ሺ፰፻፶፫ ትሑ ። ወደከተማ ፡ ወይም ፡ ወደገጠር ፡ ሰዎቹን ፡ ለመውጋት ፡ ብትሄዱ ፡ ዕርቅ ፡ ለማድረግ ፡ ጥሯቸው ። በውስጧ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ቢቀበሉዋችሁ ፡ በርም ፡ ቢከፍቱላችሁ ፡ እንደ ፡ ባሮች ፡ ይሁኑዋችሁ ። ግብርም ፡ ይገብሩላችሁ ። (ዘዳ ፡ ፳ ፡ ፲ - ፲፪) ።

፩ሺ፰፻፶፬ ዕርቅንም ፡ ለማድረግ ፡ ባይቀበሉዋችሁ ፡ ፈጽመውም ፡ ቢወጉዋችሁ ፡ አስጨንቃችሁ ፡ ውጓቸው ። ፈጣሪያችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጥልላችኋል ።

፩ሺ፰፻፶፭ ወደእናንተም ፡ ቢማጠኑ ፡ ይቅር ፡ በሏቸው ። እግዚአብሔር ፡ ይቅር ፡ የሚሉ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ እነርሱንም ፡ ይቅር ፡ ይሏቸዋልና ፡ (ማቴ ፡ ፭ ፡ ፯) ፡ ብሏልና ። ለጋስ ፡ ለሆነ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለባሮቹ ፡ ይቅርታን ፡ ስላስተማራቸው ፡ ምስጋና ፡ ይገባል ። ደቀ ፡ መዛሙርትም፡ ጌታችንን ፡ ኤልያስ ፡ እንዳደረገ ፡ እሳት ፡ ከሰማይ ፡ ትውረድና ፡ ታቃጥላቸው ፡ ልትል ፡ እንወዳለን ፡ ባሉት ፡ ጊዜ ፡ እናንተ ፡ የማን ፡ መንፈስ ፡ እንደሆናችሁ ፡ አታውቁም ? ብሎ ፡ ከለከላቸው ። (ሉቃ ፡ ፱ ፡ ፶፬ - ፶፮) ። ሰው ፡ ይቅር ፡ በማለትና ፡ ሰውን ፡ በመውደድ ፡ ፈጣሪውን ፡ ይመስለዋልና ። ክርስቲያንም ፡ ከሌሎቹ ፡ ይለያል ።

፩ሺ፰፻፶፮ ሥርዋጽ ፡ ትሑ ። በሩን ፡ እስኪከፍቱልህ ፡ ድረስ

ወንበርከ ፡ ላዕሌሃ ፡ ብዙኀ ፡ መዋዕለ ፡ ከመ ፡ ትትቃተል ፡ እስከ ፡ ያርኅዉ ፡ ለከ ፡ ኢትግዝም ፡ አእዋማሃ ፡ እስመ ፡ ዕፀወ ፡ ገዳም ፡ ኢይክሉ ፡ ጐይየ ፡ እምኔክሙ ። ወለዕፅሰ ፡ እንተ ፡ ኢትፈሪ ፡ ግዝምዋ ፡ ወጽብአዎሙ ፡ ለሰብእ ፡ ዘኢሃ ፡ እስከ ፡ ትመውእዎሙ ።

፩ሺ፭፻፶፯ ትሒ ፡ ዘ፲ወ፬ቱ ፡ ወእምከመ ፡ ኀለፍክሙ ፡ ኀበ ፡ ሀገረ ፡ እኂዊክሙ ፡ ኢታሕሥሙ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ወተማየጡ ፡ እምኔሆሙ ፡ እክለ ፡ ወማየ ፡ በብሩር ፡ ለሲሳይክሙ ፡ ወለስቴክሙ ፡ ከመ ፡ ይባርከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዕሌክሙ ።

፩ሺ፭፻፶፰ መጅ ፡ ፲ወ፰ቱ ፡ ወለእመ ፡ ተማየጠ ፡ ፩ደ ፡ እሱረ ፡ እምዘአስሮ ፡ በንዋይ ፡ እሙር ፡ ወለእመ ቦቱ ፡ ንዋይ ፡ ለዘተአስረ ፡ የሀቦ ፡ ሤጠ ፡ ዘአሁ ፡ ዘቦቱ ፡ ተማየጦ ፡ ወይማየጥ ፡ ነፍሰ ፡ ዘአሁ ፡ ቦቱ ፡ ወይኩን ፡ ግዑዘ ። ወለእመ ፡ ኀጥአ ፡ ይግበር ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ ዘተማየጦ ፡ ከመ ፡ ዓሳብ ፡ እንዘ ፡ ይትጌበር ፡ እስከ ፡ ይፈዲ ፡ ሤጠ ፡ ዘአሁ እምዓስቡ ፡ እምድኅረ ፡ ተሰነአዉ ፡ በዝንቱ ፡ በቅድመ ፡ ሰብእ ።

፩ሺ፭፻፶፱ ትሒ ፡ ዘ፲ወ፫ቱ ፡ ወለእመ ፡ ጐየ ፡ ኀቤክሙ ፡ ጐያዪ ፡ ኢታግብእዎ ፡ ኀበ ፡ እግዚኡ ፡ ወይንበር ፡ ምስሌክሙ ፡ ኀበ ፡ ፈቀደ ፡ ውስተ ፡ ፩ዱ ፡ እምእህጉሪክሙ ፡ ወኢትግፍዕዎ ።

፩ሺ፭፻፷ ጠስ ፡ ፵ ፡ ወለምህርካኒ ፡ ይንሥኡ ፡ ሳድስተ ፡ እዴሃ ፡ ለቤተ ፡ መዛግብት ፡ ዘውስተ ፡ ወለዘተርፈ ፡ ይክፍልዎ ፡ በዕሩይ ፡ ለሊቃናት ፡ ወመኳንንት ። ወእመቦ ፡ ዘአፈድፈደ ፡ እምካልኡ ፡ መክፈልተ ፡ በስምዕ ፡ ይወስክዎ ፡ እምክፍል ፡ ዘማእከል ፡ ወቤሐሳበ ፡ ክፍል ፡ ይንሥእ ፡ ዐቃቤ ፡ ዘነዳግዎ ፡ ለዐቂበ ፡ ሠራዊት ።

፩ሺ፭፻፷፩ ፴ወ፫ቱ ፡ ወለእመቦ ፡ ዘያስተዋዲ ፡ በእንተ ፡ ኣሕሥሞተ ፡ መንግሥት ፡ በዘይመውዑ ፡ ሀረ ፡ ወይክሥት ፡ ሎሙ ፡ ምክረክሙ ፡ እው ፡ ገየ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ወሤጠ ፡ ሎሙ ፡ ንዋየ ፡ ሐቅል ፡ ይስቅልዎ ፡ ወያውዕይዎ ።

፩ሺ፭፻፷፪ ምዕራፍ ፡ ፳ቱ ። እምከመ ፡ አግብእክሙ ፡ እግዚአቤሔር ፡ ውስተ ፡ እደ ፡ ፀርክሙ ፡ በእንተ ፡ ኃጣውኢክሙ ፡ ወዔወዉክሙ ፡ ውስተ ፡ ሀገሮሙ ፡ መፍትው ፡ ለክሙ ፡ ከመ ፡ ትጽንዑ ፡ ላዕለ ፡ ሃይማኖትክሙ ። ወትፀመድዎ ፡ ለሕግ



ሀገሪቱን ፡ ከብበህ ፡ ትዋጋ ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ብትቀመጥ ፡ ዛፎችዋን ፡ አትቁረጥ ። የዱር ፡ ዕንጨቶች ፡ ከእናንተ ፡ ሊሸሹ ፡ አይችሉምና ። የማታፈራውን ፡ ዕንጨት ፡ ግን ፡ ቁረጡዋት ። የሀገሪቱንም ፡ ሰዎች ፡ ድል ፡ እስክትነሱዋቸው ፡ ድረስ ፡ ውጉዋቸው ። (ዘዳ ፡ ፳ ፡ ፲፱ - ፳)

፩ሺ፭፻፶፯ ትሂ ፡ ፲፬ ። በወንድሞቻችሁ ፡ ሀገር ፡ ብታልፉ ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ አትሥሩ ። እግዚአብሔር ፡ እናንተን ፡ ይባርካችሁ ፡ ዘንድ ፡ ለምግባችሁና ፡ ለመጠጣችሁ ፡ እህልና ፡ ውሀ ፡ ከእነርሱ ፡ በብር ፡ ግዙ ። (ዘዳ ፡ ፪ ፡ ፬ - ፯) ።

፩ሺ፭፻፶፰ መጅ ፡ ፲፰ ። በታወቀ ፡ ገንዘብ ፡ ካሠረው ፡ ወገን ፡ አንዱን ፡ እሥረኛ ፡ ቢዋጅ ፡ (ቢያስፈታ) ፡ የታሰረውም ፡ ሰው ፡ ገንዘብ ፡ ቢኖረው ፡ ያስፈታበትን ፡ ገንዘብ ፡ ይስጠውና ፡ በገንዘቡ ፡ ሰውነቱን ፡ ይግዛበት ። ነጻም ፡ ይሁን ። ቢያጣ ፡ ግን ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ በዚህ ፡ ከተስማሙ በኋላ ፡ ከደመወዙ ፡ የተፈታበትን ፡ ገንዘብ ፡ እስኪከፍል ፡ ድረስ ፡ እንደምንደኛ ፡ እየሠራ ፡ በአስፈታው ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ይቆይ ።

፩ሺ፭፻፶፱ ትሄ ፡ ፲፫ ። ኮብላይ ፡ ወደእናንተ ፡ ቢኮበልል ፡ ወደ ፡ ጌታው ፡ አትመልሱት ። ከሀገሮቻችሁ ፡ በወደደው ፡ በአንዱ ፡ ውስጥ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ይኑር ። አትግፉትም ። (ዘዳ ፡ ፳፫ ፡ ፲፭ - ፲፮) ።

፩ሺ፭፻፷ ጠስ ፡ ፵ ። ከምርኮም ፡ ገንዘብ ፡ ፮ኛዋን ፡ እጅ ፡ ለውስጥ ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ይውሰድ ። የቀረውንም ፡ ለአለቆችና ፡ ለመኳንንት ፡ በትክክል ይክፈሉት ። ከሌላው ፡ ይልቅ ፡ በምስክር ፡ ድርሻን ፡ (ምርኮን) ፡ ያበዛ ፡ ቢኖር ፡ ከመካከለኛው ፡ ክፍል ፡ ይጨምሩለት ። ሠራዊትን ፡ ለመጠበቅ ፡ የተውት ፡ ሰው ፡ በድርሻው ፡ ልክ ፡ ይውሰድ ።

፩ሺ፭፻፷፩ ፴፫ ። መንግሥትን ፡ ስለመጉዳት ፡ ጠላቶች ፡ ድል ፡ በሚነሡ ፡ ሁናቴ ፡ ነገር ፡ የሚሠራ ፡ ምክራችሁንም ፡ የሚገልጽላቸው ፡ ወይም ፡ ወደእነርሱ ፡ የሸሸና ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ የሸጠላቸው ፡ ቢኖር ፡ ይስቀሉት ። ያቃጥሉትም ።

፩ሺ፭፻፷፪ አምስተኛ ፡ ምዕራፍ ። ስለ ፡ ኃጢአታችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጠላቶቻችሁ ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ቢሰጣችሁ ፡ ወደሀገራቸውም ፡ ቢማርኳችሁ ፡ በሃይማኖታችሁ ፡ ልትድኑ ፡ ይገባችኋል ። ሕጋችሁንም ፡ በመብልና ፡ በመጠጥ ፡ በሕግ ፡ ሥር

አንቀጽ ፡ ፵፯ ።

ክሙ ፡ በመብልዕኒ ፡ ወበመስቴ ፡ ወበኵሉ ፡ ሥርዓተ ፡ ሕግ ፡ በከመ ፡ ዳንኤል ፡ ወ፫ቱ ፡ ደቂቅ ፡ ከመ ፡ ያድኅንክሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምአናብስት ፡ ወእምእሳት ። ወይሰባሕ ፡ ስሙ በእንተ ፡ ሥነ ፡ ተእዝዞትክሙ ፡ ወያግብእክሙ ኀበ ፡ ሀገርክሙ ፡ ከመ ፡ እለ ፡ ዘከርናሆሙ ።

ስለ ፡ ብሉይና ፡ ሐዲስ ።

ዓትም ፡ ሁሉ ፡ ጠብቁት ። እንደ ፡ ዳንኤልና ፡ እንደ ፡ ፫ ፡ ደቂቅ ፡ (እንደ ፡ ሦስቱ ፡ ልጆች) ፡ ከአናብስትና ፡ ከእሳት ፡ ያድናችሁ ፡ ዘንድ ። (ዳን ፡ ፫ ፡ ፳፬ - ፳፯ ። ፮ ፡ ፲፱-፳፬) ። ስለመታዘዛችሁም ፡ መበጀት ፡ ስሙ ፡ ይመስገን ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ጠቀስናቸው ፡ ሰዎች ፡ ወደሀገራችሁ ፡ ይመልሳችሁ ፡ ዘንድ ።

## አንቀጽ ፡ ፵ወ፰ቱ ፡

በእንተ ፡ ዘይደሉ ፡ ተናግሮቱ ፡ በዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ እምብሉይ ፡ ወሐዲስ ፡ ካልእ ፡ እምዘተነግረ ፡ ውስተ ፡ አንቀጽ ፡ በበገጹ ።

፩ሺ፰፻፷፫ ወሰበ ፡ ኮነ ፡ ብእሲ ፡ ፍጡረ ፡ በነፍስ ፡ ወሥጋ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይሥርዑ ፡ ሎቱ ፡ ፪ተ ፡ ሕገጋተ ። ቀዳማዊ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ለአፈጽሞተ ፡ ምግባራቲሁ ፡ እለ ፡ በከሡት ፡ እንተ ፡ ሀለወት ፡ በእባላቲሁ ፡ ዘአፍአ ። ወካልእኒ ፡ ሕግ ፡ ለአፈጽሞተ ፡ ምግባራቲሁ ፡ ዘውስጥ ፡ እንተ ፡ ሀለዋ ፡ በሕሊናሁ ፡ ወኀይላቲሁ ፡ ወርከበታቲሁ ፡ ዘውስጥ ።

፩ሺ፰፻፷፬ ወቀዳማዊ ፡ ሕግ ፡ ይቀውም ፡ በሥርዓተ ፡ ሕግ ፡ ቀዳማዊ ፡ ዘውእቱ ፡ ሕገ ፡ ርትዕ ፡ ይትዐወቅ ፡ አሪት ፡ ወተሠርዑ ፡ በውስቴቱ ፡ ኵነኔያት ፡ ሥጋውያት ፡ ዘያስተርእዩ ፡ በእንተ ፡ ምግባራት ፡ ሥጋውያት ፡ ዘበሙ ፡ ይደሉ ፡ ፍትሕ ፡ በኀበ ፡ ፈታሕት ፡ ዘከመ ፡ ቀቲለ ፡ ቀታሊ ፡ ወተፈድዮ ፡ ዕዳ ፡ እምነ ፡ ሰራቂ ፡ ወዘቢጠ ፡ ዐማፂ ፡ ወዘተነግረ ፡ በእንቲአሁ ፡ ካልእ ፡ እምዝንቱ ። ወኵሉ ፡ ዘተነግረ ፡ በውስቴቱ ፡ ከመ ፡ ያብጽሕ ኀበ ፡ ዝንቱ ፡ ወከመ ፡ ይዘመዱ ፡ ቦቱ ፡ በምግባር ፡ መንፈሳዊ ፡ ከመ ፡ ሙሴ ፡ ወኤልያስ ፡ ትሩፋን ፡ ምግባር ።

፩ሺ፰፻፷፭ ወዳግማዊስ ፡ መንፈሳዊ ፡ ውእቱ ፡ ቀዊም ፡ በሕግ ፡ ደኃራዊ ፡ ወውእቱ ፡ ሕገ ፡ ፍጻሜ ፡ ወተሠርዐ ፡ በውስቴቱ ፡ ሕግ ፡ ልቡናዊ ፡ በእንተ ፡ ምግባራት ፡ ዘውስጥ ፡ ዘይትጌሠጽ ፡ ቦቱ ፡ ነፍሰ ፡ ሰብእ ፡ በውስቴቱ ፡ ነፍሱ ፡ ማእከሌሁ ፡ ወማእከለ ፡ ፈጣሪሁ ፡ በሥምረተ ፡ ርእሱ ፡ ዘከመ ፡ ተከልአ ፡ እመዓት ፡ ወእምነጽሮ ፡ በፍትወት ፡ ወአፍቅሮተ ፡ ፀር ፡ ወሠርዮ ፡ ለዘአበሰ ፡ ወተዐ

## አንቀጽ ፡ ፵፰ ።

በአንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ በየወገኑ ፡ ከተነገረው ፡ ሌላ ከብሉይና ፡ ከሐዲስ ፡ መጥቶ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ሊናገሩት ፡ ስለሚገባው ፡ ይናገራል ።

፩ሺ፰፻፷፫ ሰው ፡ ከነፍስና ፡ ከሥጋ ፡ የተፈጠረ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ ሁለት ፡ ሕጎች ፡ ሊሠሩለት ተገባ ። መጀመሪያው ፡ በሕዋሳተ ፡ አፍኣ ፡ ያለች ፡ በግልጽ ፡ የሚሠሩ ፡ ሥራዎችን ፡ ለማስፈጸም ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ሁለተኛውም ፡ ሕግ ፡ በሐሳቡና ፡ በኀይሉ ፡ በውስጥም ፡ በሚያገኙት፡ ነገሮች ፡ ያሉትን ፡ የውስዮ ፡ ሥራዎችን ፡ ለማስፈጸም ፡ ነው ።

፩ሺ፰፻፷፬ መጀመሪያው ፡ ሕግ ፡ በመጀመሪያው ፡ ሕግ፡ ሥርዓት ፡ ይጸናል ። ይኸውም ፡ የቀና ፡ ሕግ ፡ ነው ። ኦሪት ፡ እንደሆነች ፡ ይታወቃል ። ስለ ፡ ሥጋውያት ፡ ሥራዎች ፡ የሚገልጹ ፡ ሥጋውያት ፡ ቅጣቶችም ፡ በውስጡ ፡ ተሠሩ ። በዳኞች ፡ ዘንድ ፡ ፍርድ ፡ የሚገባቸው ። ይኸውም ፡ ነፍስ ገዳይን ፡ እንደመግደል ፡ ከሌባም ፡ ገንዘብን ፡ እንደመክፈል ፡ ዓመፀኛንም ፡ እንደመግረፍ ፡ ያለ ፡ ነው ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ስለእርሱ ፡ የተነገረው ፡ ነው ። በውስጡ ፡ የተነገረው ፡ ሁሉ ፡ ወደዚህ ፡ ያደርስ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። በሥራ ፡ ፍጹማን ፡ እንደሆኑ ፡ እንደ ፡ ሙሴና ፡ እንደ ፡ ኤልያስ ፡ በመንፈሳዊ ፡ ሥራም ፡ ስሙዳን ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

፩ሺ፰፻፷፭ ሁለተኛው ፡ ግን ፡ መንፈሳዊ ፡ ነው ። በኋለኛው ፡ ሕግ ፡ መጽናት ፡ ነው ። እርሱም ፡ የመጨረሻ ፡ ሕግ ፡ ነው ። ሰው ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ በእርሱና ፡ በፈጣሪው ፡ መካከል ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡ ስለሚገሥጽባቸው ፡ ውስጣውያን ፡ ሥራዎች ፡ ልቡናዊ ፡ ሕግ ፡ በውስጡ ፡ ተጽፏል ። ይኸውም ፡ ከቍጣና ፡ በፍትወት ፡ ከማየት ፡ እንደመከልከል ፡ ጠላትን ፡ እንደመው

አንቀጽ ፡ ፵፭ ።

ቅቦ ፡ እምጽጋብ ፡ ወስካር ፡ ወእትሕቶ ፡ ርእስ ፡ ለኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ወዛቲ ፡ ይእቲ ፡ እምነሶንኤያት ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ይፈትሕ ፡ ሰብእ ፡ ላዕለ ፡ ነፍሱ ፡ በሥምረተ ፡ ልቡ ፡ ዘይፈቅድ ፡ ይኩን ፡ ብእሲ ፡ ፍጹመ ፡ ወኢኮነት ፡ ይእቲ ፡ እምነሶንኤያት ፡ እንተ ፡ ይፈትሖ ፡ ባቲ ፡ መኳንንት ፡ ላዕለ ፡ ሰብእ ፡ በግብር ።

፩ሺ፫፻፶፯ ወኢተሠርዐ ፡ ዘደኃራዊ ፡ ሕግ ፡ እብተሎቱ ፡ ለዘተነግረ ፡ በሕግ ፡ ቀዳማዊ ፡ እስመ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ "ኢመጻእኩ ፡ ከመ ፡ እሥዐሮ ፡ ለሕግ ፡ እላ ፡ ከመ ፡ እፈጽሞ ።" ወይእዜኒ ፡ እንከሰ ፡ ኢተሐጎገ ፡ እሰርዮተ ፡ ፍትሐሙ ፡ ለፈታሕት ። ወበእንተዝ ፡ ተጽሕፈ ፡ ውስተ ፡ ዓሥር ፡ ምዕራፍ ፡ ዘድስቅ ፡ ፍጡን ፡ ሥረዩ ፡ ኃጣውአ ፡ እኃዊክሙ ፡ እኮ ፡ ዘንብል ፡ ዘንተ ፡ ስፈታሕት ። ወስምዐ ፡ ኮነ ፡ በውስተ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ ወካልእኒ ፡ ላዕለ ፡ ብዙኅ ፡ እምፍትሐታት ፡ በዘነበረ ፡ እምኔሃ ፡ ውስተ ፡ አሪት ፡ ወለእመ ፡ ተደርሰ ፡ ደለወ ፡ ከመ ፡ ይንበር ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ በኵሉ ፡ ዘነበረ ፡ ውስተ ፡ ዘቀዳሚ ፡ ሕግ ፡ እምግብር ፡ ለፈታሕት ፡ በእንተ ፡ ፈቲሕ ፡ ዘቦቱ ፡ ይፈትሑ ፡ ላዕለ ፡ ሰብእ ፡ በእንተ ፡ ምግባራት ፡ ግሁዳት ። ወበኵሉ ፡ ዘተነግረ ፡ በሕግ ፡ ደኃራዊ ፡ እምነ ፡ ገሥጸተ ፡ ብእሲ ፡ በሕሊናሁ ፡ በኵሉ ፡ ክብር ፡ ሀሎ ፡ በአንቀጽ ፡ ዚአሁ ።

፩ሺ፫፻፶፰ ወናሁ ፡ ተነግረ ፡ በዝንቱ ፡ አንቀጽ ፡ እምነ ፡ ውእቱ ፡ ቃላት ፡ ፍሉጣት ፡ ካልእ ፡ እምዘ ፡ ተነግረ ፡ በእናቅጽ ። ለቀዳማዊሰ ፡ እምቅድመ ፡ ተናግሮቱ ፡ ንበል ፡ ከመ ፡ ሕግ ፡ ቀዳማዊ ፡ ሶበ መጽአ ፡ ሕግ ፡ ደኃራዊ ፡ ኢጸንዐ ፡ ሕግ ፡ ቀዳማዊ ፡ በኵለንታሁ ፡ ወኢበጠለ ፡ ኵለንታሁ ፡ እላ ፡ ኀበ ፡ ፪ቱ ፡ ክፍል ፡ ተከፍለ ። ፩ዱሰ ፡ ክፍል ፡ ተርፈ ፡ ኀበ ፡ ሀላዌሁ ፡ እስመ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ ኮነኔ ፡ ፍትሑ ፡ ሀልው ፡ ዘኢይትማሰል ፡ ምስለ ፡ ካልአኒሁ ፡ እምግባራተ ፡ ትሩፋት ፡ ዘውእቱ ፡ እምልኮ ፡ ፈጣሪ ፡ ዘእንበለ ፡ ፍጡራን ፡ ወተከልአ ፡ እምቀቲል ፡ ወዝሙት ። ወ፩ዱኒ ፡ ክፍል ፡ ተፀርዐ ፡ በምልኡ ፡ እስመ ፡ ግብረ ፡ ቀዊም ፡ ቦቱ ፡ ተፀርዐ ፡ በምልኡ ፡ ወዘይትፈቀድ ፡ እምኔሁ ፡ ኮነ ፡ ዘከመ ፡ ሕርመተ ፡ ሐሪውያ ፡ እስመ ፡ መፍትድ ፡ እምኔሁ ፡ ውስተ

ስለ ፡ ብሉይና ፡ ሐዲስ ።

ደዶ ፡ የበደለን ፡ ይቅር ፡ እንደማለት ፡ ከጥጋብና ፡ ከስካር ፡ እንደመጠበቅ ፡ ራስንም ፡ ለሰውሁሉ ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ እንደማድረግ ፡ ያለ ፡ ነው ። ይችውም ፡ ከቅጣቶች ፡ ወገን ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ሊሆን ፡ የወደደ ፡ ሰው ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ በሰውነቱ ፡ ላይ ፡ ሰው ፡ የሚፈርድባት ፡ ናት ። መኳንንት ፡ በግድ ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ከሚፈርዷቸው ፡ ቅጣቶች ፡ ወገን ፡ አይደለችም ።

፩ሺ፫፻፶፯ በፊተኛው ፡ ሕግ ፡ የተነገረውን ፡ ማፍረስ ፡ በኋለኛው ፡ ሕግ ፡ አልተጻፈም ። ጌታችን ፡ ሕግን ፡ ልፈጽመው ፡ እንጂ ፡ ልሽረው ፡ አልመጣሁም ፡ ብሏልና ። (ማቴ ፡ ፭ ፡ ፲፯) ። እንግዲያውስ ፡ ዛሬም ፡ የዳኞችን ፡ ፍርድ ፡ መሻር ፡ አልታዘዘም ። ስለዚህ ፡ በድስቅ ፡ በ፲ኛው ፡ ምዕራፍ ፡ ተጽፏል ። የወንድሞቻችሁን ፡ በደል ፡ ፈጥናችሁ ፡ ይቅር ፡ በሉ ። ይህንም ፡ ለዳኞች ፡ የምንናገር ፡ አይደለንም ። በዚህም ፡ ውስጥ ፡ መጽሐፍ ፡ ምስክር ፡ ሆነ ። ሌላውም ፡ ከርሱዋ ፡ ወጥቶ ፡ በኦሪት ፡ በተጻፈው ፡ ከፍርድ ፡ ወገን ፡ በብዙ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ተገለጹ ፡ ሥራዎችም ፡ ዳኞች ፡ ከሥራ ፡ ወገን ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ስለሚፈርዱበት ፡ ፍርድ ፡ በቀደመው ፡ ሕግ ፡ በተጻፈው ፡ ሁሉ ፡ ድርሰት ፡ ቢደረስ ፡ ከዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ጋራ ፡ ሊቀመጥ ፡ ተገባ ። በሥራው ፡ ሁሱ ፡ በሐሳቡ ፡ ሰውን ፡ ከመገሠጽ ፡ የተነግ ፡ በኋለኛው ፡ ሕግ ፡ የተጻፈው ፡ ሁሉ ፡ በእርሱው ፡ አንቀጽ ፡ አለ ።

፩ሺ፫፻፶፰ በየአንቀጹ ፡ ከተነገረው ፡ ሌላ ፡ ልዩ ፡ ከሆኑ ፡ ቃላት ፡ መጥቶ ፡ እነሆ ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ተነገረ ። የመጀመሪያውን ፡ ሕግ ፡ ከመናገሩ ፡ አስቀድሞ ፡ እንደ ፡ መጀመሪያው ፡ ሕግ ፡ ኋለኛው ፡ ሕግ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ የፊተኛው ፡ ሕግ ፡ በ፪ ፡ ክፍል ፡ ተከፈለ ፡ እንጂ ፡ መላውም ፡ አልተሻረም ። መላውም ፡ አልጸናም ፡ እንበል ። አንደኛው ፡ ክፍል ፡ ባለበት ፡ ጸና ። ከትሩፋት ፡ ሥራዎች ፡ ወገን ፡ ከሌሎች ፡ ጋራ ፡ የማይመሳሰል ፡ የፍርዱ ፡ ቅጣት ፡ ሁልጊዜ ፡ ይኖራልና ። ይኸውም ፡ ከፍጡራን ፡ ለይቶ ፡ ፈጣሪን ፡ ማምለክ፡ ከመግደልና ፡ ከመሰሰንም ፡ መከልከል ፡ ነው ። ፩ኛውም ፡ ክፍል ፡ በሙሉ ፡ ተሻረ ። በእርሱ ፡ ጸንቶ ፡ መኖር ፡ በሙሉ ፡ ተሽሯልና ። ከእርሱ ፡ የሚሻውም ፡ ከዕሪያ ፡ እንደመከልከል ፡ ያለ ፡ ነበር ። በቀደመው ፡ ሕግ ፡ ከእርሱ ፡ የሚሻው ፡

ሕግ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኮነ ፡ ከመ ፡ ኢይደመሩ ፡ ሕዝበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስለ ፡ አሕዛብ ፡ አለ ፡ ኢያመልክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘበኀቤሆሙ ፡ ሀሎ ፡ ብዙኅ ፡ እሕርው ፡ ከመ ፡ ኢይትመየጡ ፡ ኀበ ፡ እምልኮቶሙ ፡ ወልማዳቲሆሙ ፡ እኪት ።

፩ሺ፰፻፳፰ ወሶበ ፡ ሰፈነ ፡ እሚን ፡ ላዕለ ፡ ኩሉ ፡ አሕዛብ ፡ ወኢተርፉ ፡ ዘእንበለ ፡ ኀዳጣን ፡ ዐላውያን ፡ በፈቃድ ፡ እምላካዊ ፡ ደለወ ፡ ፈቂድ ፡ ኀበ ፡ ተጋብእቶሙ ፡ ለመሃይምናን ፡ ወደለወ ፡ እፅርእቱ ፡ ለዘይከልእ ፡ ወለዘይከልአዎሂ ። ወ፩ዱ ፡ ከፍል ፡ ኮነ ፡ ፍጹመ ፡ በተወስኮ ፡ ላዕሌሁ ፡ ዘከመ ፡ ገቢረ ፡ ሠናይ ፡ ለፍቁር ፡ ወለጸላእት ፡ ካዕበ ፡ ወሕጹጽስ ፡ ዘኮነ ፡ ሕጹጸ ፡ አምፍጻሜ ፡ ኮነ ፡ ፍጹመ ፡ ዘከመ ፡ ገቢረ ፡ ሠናይ ፡ በዕለተ ፡ ስንበታት ፡ ዘተአዘዘ ፡ ቀዳሚ ፡ ኀዲገ ፡ ኩሉ ፡ ግብር ፡ ውስቴቶን ። ወ፩ዱ ፡ ክፍል ፡ ኮነ ፡ ሥጋዊ ፡ ወፈለሰ ፡ ኀበ ፡ ግብር ፡ መንፈሳዊ ፡ ወኮነ ፡ ህየንተ ፡ አንጽሖ ፡ ሥጋ ፡ በማያት ፡ ወደማት ፡ እንጽሖ ፡ ነፍስ ፡ በንስሓ ፡ ወሥርዓታቲሃ ። ወህየንተ ፡ ተስፋ ፡ መንግሥተ ፡ ምድር ፡ ወሠናያቲሃ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ወዘለዓለም ፡ ተድላሃ ።



የእግዚአብሔር ፡ ወገኖች ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከማያመልኩት ፡ በእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡ ዕሪያ፡ ካላቸው ፡ ከአሕዛብ ፡ ጋራ ፡ እንዳይገናኙ ፡ ነበርና ። ወደአምልኮታቸውና ፡ ወደክፉ ፡ ልማዳቸው ፡ እንዳይመለሱ ።

፩ሺ፰፻፳፰ ሃይማኖት ፡ በአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ በሰፈነ ፡ ጊዜ ፡ ከጥቂቶችም ፡ ዐላውያን ፡ በቀር ፡ በአልቀሩ ፡ ጊዜ ፡ በአምላካዊ ፡ ፈቃድ ፡ ምእመናንን፡ ወደመሰብሰብ ፡ መሻት ፡ ተገባ ። የሚከለክለውንና ፡ የሚከለክሉትን ፡ ነገርም ፡ መሻር ፡ ተገባ ። አንደኛውም ፡ ክፍል ፡ ተጨምሮበት ፡ ፍጹም ፡ ሆነ ። ለወዳጅ ፡ ዳግመኛም ፡ ለጠላት ፡ በጎ ፡ እንደመሥራት ፡ ያለው ፡ ነው ። ከፍጹምነት ፡ ሕፀፅ ፡ የነበረውም ፡ ፍጹም ፡ ሆነ ። ይኸውም ፡ ቀድሞ ፡ ሥራን ፡ ሁሉ ፡ መተው ፡ በታዘዘባቸው ፡ ሰንበታት ፡ ቀን ፡ በጎ ፡ እንደመሥራት ፡ ያለ ፡ ነው ። አንዱ ፡ ክፍል ፡ ሥጋዊ ፡ ነበረ ። ወደመንፈሳዊም ፡ ሥራ ፡ ተላለፈ ። ሥጋን ፡ በውኃና ፡ በደም ፡ ስለማንጻት ፡ ፈንታ ፡ በንስሐና ፡ በሥርዓቶቿ ፡ ነፍስን ፡ ማንጻት ፡ ሆነ ። የምድር ፡ መንግሥትንና ፡ ተድላ ፡ ደስታዋን ፡ ተስፋ ፡ ስለማድረግ ፡ ፈንታም ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይንና ፡ የዘለዓለም ፡ ተድላዋን ፡ ተስፋ ፡ ማድረግ ፡ ሆነ ።

፩ሺ፰፻፳፱ ወይእዜኒ ፡ ኢይትፈቀዳ ፡ በዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ ኩሎን ፡ ትእዛዛት ፡ አለ ፡ ቀደማ ። ወዘይትፈቀድስ ፡ አምብሔረ ፡ ኦሪት ፡ ዳግማዊ ፡ ዘይቤ ፡ ቃሉ ፡ ለልዑል ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ እነ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክከ ፡ ኢትግበር ፡ ለከ ፡ አምላከ ፡ ዘእንበሌየ ። ወኢትግበር ፡ ለከ ፡ ግልፈዋተ ፡ ወኢእምሳላተ ፡ ዘውስተ ፡ ሰማይ ፡ ዘላዕሉ ፡ ወኢዘውስተ ፡ ምድር ፡ ዘታሕቱ ፡ ወኢትስግድ ፡ ሎሙ ፡ ወኢታምልኮሙ ። እስመ ፡ እነ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክከ ። "ኢትምሐል በስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጣሪከ ፡ በሐሰት ፡ እስመ ፡ ኢያነጽሖ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዘይምሕል ፡ ስሞ ፡ በሐሰት ። "ወአክብር ፡ እባከ ፡ ወእመከ ፡ ከመ ፡ ትርከብ ፡ ሠናየ ፡ ወይኑኅ ፡ መዋዕሊከ ። "ኢትቅትል ፡ ወኢትዘሙ ፡ ኢትስርቅ ፡ ወኢትኩን ፡ ስምዐ ፡ በሐሰት ፡ ላዕለ ፡ ቢጽከ ። ወኢትፍቱ ፡ ቤተ ፡ ካልእከ ፡ ኢ ፡ ብእሲቶ ፡ ወኢገብሮ ፡ ወኢ ፡ እመቶ ፡ ወኢ ፡ እንስሳሁ ፡ ወኢ ፡ ኩሎ ፡ ዘአጥረዮ ፡ ቢጽከ ።

፩ሺ፰፻፳፱ ዛሬም ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ የቀደሙት ፡ ትእዛዛት ፡ ሁሉ ፡ አያፈለጉም ። የሚሻውስ ፡ በ፪ኛው ፡ ብሔረ ፡ ኦሪት ፡ ምስጋና ፡ ይግባውና ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጣሪህ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ። ከእኔ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ እምላክ ፡ አታድርግ ። ያለው ፡ ቃል ፡ ነው ። ጣዖቶችንም፡ ከላይ ፡ በሰማይ ፡ ያሉትን ፡ ከታችም ፡ በምድር ፡ ያሉትን ፡ ምሳሌዎች ፡ ለአንተ ፡ አታድርግ ። አትስገድላቸውም ። አታምልካቸውም ። ፈጣሪህ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ነኝና ። በፈጣሪህ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ በሐሰት ፡ አትማል ። እግዚእብሔር ፡ በሐሰት ፡ በስሙ ፡ የሚምለውን ፡ እያነፃውምና ። መልካም ፡ ነገርንም ፡ ታገኝ ፡ ዘንድ ፡ ዕድሜህም ፡ ይረዝም ፡ ዘንድ ፡ አባትና ፡ እናትህን ፡ አክብር ። እትግደል ፡ አትስስን ፡ አትስረቅ ፡ በባልንጀራህ ፡ ላይ ፡ በሐሰት ምስክር ፡ አትሁን ። የጓደኛህን ፡ ቤቱን ፡ ሚስቱንም ፡ ወንድ ፡ ባሪያውንና ፡ ሴት ፡ ባሪያውን ፡ እንስሳውንም ፡ ባልንጀራህ ፡ የገዛውን ፡ ሁሉ ፡

አንቀጽ ፡ ፵፩ ።

፩ሺ፫፻፸ ወዛቲ ፡ ትእዛዛተ ፡ ፍትሕ ፡ እንተ ፡ ተሠርዐት ፡ ሎሙ ፡ እመቦ ፡ ዘአጥረየ ፡ ገብረ ፡ ዕብራዌ ፡ ይቅንዮ ፡ ፮ተ ፡ ዓመተ ፡ ወበሳብዕት ፡ ዓመት ፡ ያግዕዞ ፡ ወይፃእ ፡ ዘእንበለ ፡ ሤጥ ፡ ወለእመ ፡ ቦእ ፡ ምስለ ፡ ብእሲቱ ፡ ይፃእ ፡ ምስሌሃ ። ወለእመኒ ፡ ወሀቦ ፡ እግዚኡ ፡ ብእሲተ ፡ ወወለደት ፡ ሎቱ ፡ ርስ ፡ ወአዋልደ ፡ ብእሲት ፡ ወውሉዳ ፡ ይትቀነዩ ፡ ለእግዚአሙ ፡ ውእቱሰ ፡ ይፃእ ፡ ባሕቲቱ ፡ ወለእመ ፡ ይቤ ፡ ገብር ፡ አፍቀርኩ ፡ እግዚእየ ፡ ወብእሲትየ ፡ ወውሉድየ ፡ ወኢይፈቅድ ፡ ግዕዛነ ፡ ለይኩን ፡ ሎቱ ፡ ገብረ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ። ወለእመኒ ፡ ሤጠ ፡ ወለተ ፡ እመቱ ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ወለተ ፡ ገብሩ ፡ ኢትጸጎጉ ፡ እምቤቱ ፡ በከመ ፡ ይጸጎኃ ፡ አእማት ፡ ወኢያግባ ፡ ለሕዝብ ፡ ነኪር ።'

፩ሺ፫፻፸፩ ወለእመ ፡ ተበአሱ ፡ ፪ቱ ፡ ሰብእ ፡ ወዘበጦ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ለካልኡ ፡ አው ፡ ገፍዖ ፡ ወኢሞተ ፡ ወሰከበ ፡ ውስተ ፡ ምስካቡ ፡ ወእምዝ ፡ ተንሥአ ፡ ወአንሶሰወ ፡ ጽጐ ፡ ተመርጕዞ ፡ በትረ ፡ ይድኅን ፡ ዘዘበጦ ፡ አላ ፡ የሀቦ ፡ ህየንተ ፡ ዕርዓቲሁ ፡ ወየሀቦ ፡ ዓስበ ፡ ለዐቃቤ ፡ ሥራይ ። ወእመ ፡ ዘበጠ ፡ ብእሲ ፡ ዓይነ ፡ ገብሩ ፡ አው ፡ ዓይነ ፡ እመቱ ፡ ወአጥፍአ ፡ ዓይኖ ፡ ያግዕዞ ፡

፩ሺ፫፻፸፪ ወለእመ ፡ ወግአ ፡ ላሕሙ ፡ ብእሴ ፡ ወቀተሎ ፡ ይገርዎ ፡ ለላሕም ፡ ወኢይብልዑ ፡ ሥጋሁ ፡ ወይድኅን ፡ በዓለ ፡ ላሕም ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ላሕም ፡ ዘይወግእ ፡ እምትማልም ፡ ወእምቅድመ ፡ ትማልም ፡ ወአስምዑ ፡ ላዕለ ፡ እግዚኡ ፡ ወኢዐቀቦ ፡ ላሕሙኒ ፡ ይትወገር ፡ በእብን ፡ ወይቅትልዎ ፡ ካዕበ ፡ ለእግዚኡ ። ወለእመ ፡ ፈትሑ ፡ ላዕሌሁ ፡ ዕዳ ፡ ይፍዲ ፡ ቤዛ ፡ ነፍሱ ፡ ዘኀሠሡ ፡ እምኔሁ ። ወለእመ ፡ ቀተለ ፡ ላሕም ፡ ገብረ ፡ አው ፡ አመተ ፡ የሀቡ ፡ ሤጦ ፡ ለእግዚኡ ፡ ወይውግርዎ ፡ ለላሕም ።

፩ሺ፫፻፸፫ ወእመቦ ፡ ብእሲ ፡ ዘከሠተ ፡ ግበ ፡ አው ፡ ከረየ ፡ ዓዘቅተ ፡ ወኢከደኖ ፡ አፉሁ ፡ ወጸድፈ ፡ ውስቴቱ ፡ ላሕም ፡ ወእመኒ ፡ አድግ ፡ እግዚአ ፡ ዓዘቅት ፡ ይፍዲ ፡ ለእግዚኡ ፡ ወገደላሁኒ ፡ ይንሣእ ፡ ውእቱ ። ወላሕም ፡ ለእመ ፡ ወግአ ፡

ስለ ፡ ብሉይና ፡ ሐዲስ ።

አትመኝ ። (ዘፀ ፡ ፳ ፡ ፫ - ፲፯) ።

፩ሺ፫፻፸ የተሠራችላቸው ፡ የፍርድ ፡ ትእዛዝ ፡ ይህች ፡ ናት ። ዕብራዊ ፡ ባሪያ ፡ የገዛ ፡ ቢኖር ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ይግዛው ፡ በ፯ኛውም ፡ ዓመት ፡ ነጻ ፡ ያውጣው ። ያለዋጋም ፡ ይውጣ ። ከሚስቱም ፡ ጋር ፡ ቢገባ ፡ ከእርስዋ ፡ ጋር ፡ ይውጣ ። ጌታው ፡ ሚስት ፡ ቢያጋባውም ፡ ወንድ ፡ ልጅና ፡ ሴቶች ፡ ልጆችም ፡ ብትወልድለት ፡ ሚስቱና ፡ ልጆቿ ፡ ለጌታቸው ፡ ይገዙ ። እርሱ ፡ ግን ፡ ብቻውን ፡ ይውጣ ። ባሪያውም ፡ ጌታዬንና ፡ ሚስቴን ፡ ልጆቼንም ፡ እወድዳለሁ ፡ ነጻነትንም ፡ አልሻም ፡ ቢል ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ባሪያ ፡ ይሁነው ። የሴት ፡ ባሪያውንም ፡ ልጅ ፡ ቢሸጥ ፡ ይህችም ፡ የወንድ ፡ ባሪያው ፡ ልጅ ፡ ናት ። ሴቶች ፡ ባሮች ፡ ትልወት ፡ ሁነው ፡ እንደሚስጡ ፡ ከቤቱ ፡ አትውጣ ። ለባዕድ ፡ ወገንም ፡ አይሽጣት ።

፩ሺ፫፻፸፩ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ቢጣሉና ፡ ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ ሌላውን ፡ ቢመታው ፡ ወይም ፡ ቢገፋው ፡ ባይሞትም ፡ በአልጋውም ፡ ላይ ፡ ቢተኛ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ተነሥቶ ፡ በትር ፡ እየተመረኰዘ ፡ ጥግ ፡ ለጥግ ፡ ቢሄድ ፡ የመታው ፡ ይድናል ። ሥራ ፡ የፈታበትን ፡ ይስጠው ፡ እንጂ ። የወጌሻውንም ፡ ዋጋ ፡ ይስጥ ። ሰው ፡ የወንድ ፡ ባሪያውን ፡ ዓይን ፡ ወይም ፡ የሴት ፡ ባሪያውን ፡ ዓይን ፡ መትቶ ፡ ቢያጠፋ ፡ ስለ ፡ ዓይኑ ፡ ፈንታ ፡ ነጻ ፡ ያውጣው ።

፩ሺ፫፻፸፪ በሬ ፡ ሰው ፡ ወግቶ ፡ ቢገድል ፡ በሬውን ፡ ይውገሩት ። ሥጋውንም ፡ አይብሉት ። ባለበሬውም ፡ ይዳን ። በሬው ፡ ከትናትና ፡ ከትናትናም በፊት ፡ የሚዋጋ ፡ ቢሆን ፡ በባለቤቱም ፡ ቢያዳኙበት ፡ ባይጠብቀውም ፡ በሬው ፡ በድንጋይ ፡ ይወገር ። ባለቤቱንም ፡ ደግሞ ፡ ይግደሉት ። የነፍስ ፡ ዋጋ ፡ ቢፈርዱበትም ፡ ከእርሱ ፡ የፈለጉትን ፡ የነፍሱን ፡ ዋጋ ፡ ይክፈል ። በሬ ፡ ወንድ ፡ ባሪያ ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ባሪያ ፡ ቢገድል ፡ ዋጋውን ፡ ለጌታው ፡ ይስጡ ፡ በሬውንም ፡ ይውገሩት ።

፩ሺ፫፻፸፫ ጉድጓድ ፡ የከፈተ ፡ ወይም ፡ የውሀ ፡ ጉድጓድ ፡ የቈፈረ ፡ ቢኖር ፡ አፉን ፡ ባይገጥመው ፡ ላም ፡ ወይም ፡ አህያ ፡ በውስጡ ፡ ቢወድቅ ፡ ባለ ጉድጓዱ ፡ ይክፈል ። የሞተውንም ፡ እርሱ ፡ ይውሰድ ። በሬ ፡ የሌላውን ፡ ሰው ፡ በሬ ፡ ቢወጋ ፡

አንቀጽ ፡ ፵፰ ።

ላሕመ ፡ ካልእ ፡ ብእሲ ፡ ወሞተ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ይሣየጥዎ ፡ ለሕያው ፡ ላሕም ፡ ወይትካፈሉ ፡ ሤጦ ፡ ወሤጠ ፡ ምዉት ፡ ካዕበ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ወጋኤ ፡ ላሕሙ ፡ እምትማልም ፡ ወእምትካት ፡ ወኢዐቀቦ ፡ እግዚእ ፡ ዚእሁ ፡ ይፍዲ ፡ ላሕመ ፡ ተክለ ፡ ላሕም ፡ ወገይላ ፡ ዘሞተ ፡ ውእቱ ፡ ይነሣእ ።

፩ሺ፰፻፸፬ ወለእመ ፡ ተውሕሰ ፡ ብእሲ ፡ እምቢጹ ፡ እንስሳ ፡ ወተሰብረ ፡ ወሞተ ፡ ወኢሀለወ ፡ እውሓሲ ፡ ምስሌሁ ፡ ለእግዚእ ፡ ንዋይ ፡ ይፍዲ ። ወእመሰ ፡ ሀለወ ፡ እግዚእ ፡ ንዋይ ፡ ምስሌሁ ፡ ኢይፍዲ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘተዓሰባ ፡ በዓስብ ፡ ወሞተት ፡ ዘእንበለ ፡ ተዓስቦት ።

፩ሺ፰፻፸፭ ወለእመቦ ፡ ዘአስሐታ ፡ ለድንግል ፡ እንተ ፡ ኢተሐፅየት ፡ ወሰከበ ፡ ምስሌሃ ፡ የሀብ ፡ ሕዬሃ፡ ወትኩኖ ፡ ብእሲተ ። ወለእመ ፡ አበየ ፡ አቡሃ ፡ ከመ ፡ ያስተዋስባ ፡ሎቱ ፡ የሀባ ፡ ሕዬሃ ፡ በአምጣነ ፡ ሕዬሆን ፡ ለደናግል ።

፩ሺ፰፻፸፮ ወለመኳንንት ፡ ኢትሕምዮሙ ፡ ወኢትሰርፍ ፡ ላዕለ ፡ መኰንነ ፡ ሕዝብከ ፡ ወኢታስተጸግር ፡ ቀዳምያተ ፡ ዓውደ ፡ እክልከ ፡ ወምክያዳቲከ ፡ ወበኵረ ፡ ውሉድከ ፡ ወረስዮሙ ፡ ሊተ ። ወከማሁ ፡ ግበር ፡ ሊተ ፡ ላሕመከ ፡ ወበግዐከ ፡ ወእድግከ ፡ ወዘተወልደ ፡ እምኔሆሙ ፡ ሰቡዐ ፡ መዋዕለ ፡ ይንበር ፡ ምስለ ፡ እሙ ፡ ወእመ ፡ ሳምንት ፡ ዕለት ፡ አምጽእ ፡ ሊተ ።

፩ሺ፰፻፸፯ ወለእመ ፡ ረከብከ ፡ ላሕመ ፡ ጸላኢከ ፡ ግዱፈ ፡ አው ፡ አድጎ ፡ አግብእ ፡ሎቱ ። ወለእመ ፡ ርኢከ ፡ አድግ ፡ ጸላኢከ ፡ ውዱቀ ፡ በታሕተ ፡ ፆሩ ፡ ኢትትዓደዎ ፡ እስከ ፡ ታነሥእ ፡ ምስሌሁ ። ወኢትሳተፍ ፡ በቀቲለ ፡ ጻድቅ ፡ ወንጹሕ ፡ ኢታድኅን ፡ ወሕልያነ ፡ ኢትንሣእ ፡ እስመ ፡ ሕልያን ፡ ያዐውር ፡ አዕይንተ ፡ ወይመይጥ ፡ ነገረ ፡ ርቱዕ ።

፩ሺ፰፻፸፰ ትጋ ፡ ወለእመቦ ፡ ዘአበሰ ፡ ወስሕተ ፡ በምንትኒ ፡ በቅድሳተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘእንበለ ፡ አእምሮ ፡ ያብእ ፡ ቍርባነ ፡ ህየንተ ፡ ዘአበሰ ፡ ቦቱ ፡ እምቅድሳት ፡ ወያግብእ ፡ በዲቤሁ ፡ ምስሌሁ ፡ ትኅምሥቶ ፡ ወይሰድ ፡ ኀበ ፡ ካህን ፡ ወያስተሥሪ ፡ በእንቲአሁ ፡ በቅድሳት ፡ ዘቍርባን ፡ ወይትኀደግ ፡ሎቱ ።

ስለ ፡ ብሉይና ፡ ሐዲስ ።

ከእነርሱ ፡ አንዱ ፡ ቢሞት ፡ ያልሞተውን ፡ በሬ ፡ ሸጠው ፡ ዋጋውን ፡ ይካፈሉ ። ዳግመኛም ፡ የሞተውን ፡ በሬ ፡ ዋጋ ። በሬው ፡ ከትናትና ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ተዋጊ ፡ ቢሆን ፡ ጌታውም ፡ ባይጠብቀው ፡ በበሬው ፡ ምትክ ፡ በሬ ፡ ይክፈል ። የሞተውን ፡ ሥጋ ፡ እርሱ ፡ ይውሰድ ። (ዘፀ ፡ ፳፩ ፡ ፴-፴፮) ።

፩ሺ፰፻፸፬ ሰው ፡ ከጓደኛው ፡ እንስሳ ፡ ቢዋስ ፡ ቢሰበርና ቢሞት ፡ ያዋሰውም ፡ ሰው ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ባይኖር ፡ ለባለገንዘቡ ፡ ይክፈል ። የገንዘቡ ፡ ጌታ ፡ አብሮት ፡ ቢኖር ፡ ግን ፡ አይክፈል ። በኪራይ ፡ የተከራያት ፡ ብትሆንም ፡ ያለኪራይ ፡ ሞተች ።

፩ሺ፰፻፸፭ ያልታጨችውን ፡ ልጃገረድ ፡ ያሳተና ፡ አብሯት ፡ የተኛ ፡ ቢኖር ፡ ማጫዋን ፡ ሰጥቶ ፡ ሚስት ፡ ትሁነው ። አባቷም ፡ ለእርሱ ፡ ያጋባት ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ ቢል ፡ በልጃገረዶች ፡ ማጫ ፡ ልክ ፡ ማጫዋን ፡ ይስጣት ። (ዘፀ ፡ ፳፪ ፡ ፲፮-፲፰) ።

፩ሺ፰፻፸፮ መኳንንትን ፡ አትሚቸው ። የወገንህን ፡ ሹም ፡ አትሳደብ ። የአህልህንና ፡ የወይንህን ፡ ቀዳምያትም ፡ የልጅህንም ፡ በኵር ፡ ወደኋላ ፡ አትበል ። ለእኔም ፡ አድርጋቸው ። እንደዚሁም፡ ላምህንና ፡ በግህን ፡ አህያህንም ፡ ለእኔ ፡ አድርግ ። ከእነርሱም ፡ የተወለደው ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ከእናቱ ፡ ጋር ፡ ይቆይ ። በስምንተኛውም ፡ ቀን፡ ለእኔ ፡ አምጣልኝ ። (ዘፀ ፡ ፳፪ ፡ ፳፰-፴፩) ።

፩ሺ፰፻፸፯ የጠላትህን ፡ በሬ ፡ ወይም ፡ አህያውን ፡ ጠፍቶ ፡ (ኮብልሎ) ፡ ብታገኘው ፡ መልስለት ። የጠላትህንም ፡ አህያ ፡ ከጭነቱ ፡ በታች ፡ ወድቆ ፡ ብታይ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ አስከታናሣው ፡ ድረስ ፡ አትለፈው ። ጻድቁንም ፡ በመግደል ፡ አትተባበር ። ንጹሐተኛውንም ፡ አታድን ። መማለጃም ፡ አትቀበል ። መማለጃ ፡ ዓይንን ፡ አሳውሮ ፡ ቀናውን ፡ ነገር ፡ ይለውጣልና ። (ዘፀ ፡ ፳፫ ፡ ፬-፱) ።

፩ሺ፰፻፸፰ ትጋ ። ሳያውቅ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቅድሳት፡ በማናቸውም ፡ የበደለና ፡ የሳተ ፡ ቢኖር ፡ ከተቀደሰው ፡ ወገን ፡ ስለበደለበት ፡ ፈንታ ፡ ቍርባን ያቅርብ ። በዓይነቱ ፡ ላይ ፡ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ አምስት ፡ አድርጎ ፡ ያግባ ። ወደካህኑም ፡ ይውሰድ ። ስለእርሱም ፡ ለቍርባን ፡ በተቀደሰው ፡ ነገር ፡ ያስተሥርይለት ። ይሠረይለታልም ። (ዘሌ ፡ ፭ ፡ ፲፮) ።

አንቀጽ ፡ ፶፫ ።

፩ሺ፰፻፸፬ ወእመቦ ፡ ዘአበሰ ፡ በአሐቲ ፡ ግብር ፡ እምዘ ፡ አሕረመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኢ.ብውሕት ፡ ለገቢር ፡ ወኢያእመረ ፡ ያብእ ፡ ቍርባነ ። ወለእመ ተኃሕለዎ ፡ ፩ዱ ፡ ለቢጹ ፡ በማኅፀንት ፡ አው ፡ በተሰናእዎ ፡ ተማባር ፡ አው ፡ ዘየምስዮ ፡ ለቢጹ ፡ አው ፡ ዘይዔምዮ ፡ አው ፡ ዘረከበ ፡ ግድፍተ ፡ አው ፡ ጕያዪተ ፡ ወክሕደ ፡ ኪያሃ ። ወዘይምሕል ፡ በአሐቲ ፡ እምነ ፡ እሉ ፡ ዙሎሙ ፡ እንተ ፡ ይገብሩ ፡ ሰብእ ፡ ወይኤብስ ፡ ባቲ ፡ ወእምከመ፡ አበሰ ፡ ያግብእ ፡ ዘተዓገለ ። ወእመኒ ፡ ዘዐመፀ ፡ አው ፡ ማኅፀንተ ፡ ዘአንበሩ ፡ ኀቤሁ ፡ አው ፡ ግድፍተ ፡ አው ፡ ጕያዪተ ፡ ዘረከበ ፡ አው ፡ ዘመሐለ ፡ ላዕሌሁ ፡ በሐሰት ፡ ያግብአ ፡ ወይወስክ ፡ ላዕሌሁ ፡ ትኅምስቶ ፡ ወየሀቦ ፡ ለዘውእቱ ፡ ሎቱ በዕለተ ፡ ቅስቱ ፡ አው ፡ በዕለተ ፡ ተአመነ ፡ በአበሳሁ ፡ ወያብእ ፡ ቍርባነ ።

፩ሺ፰፻፸፭ ወእመ ፡ ቦ ፡ ብእሲ ፡ እምደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ አው ፡ እምነኪራን ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ማእከሌሆሙ ፡ ዘይበልዕ ፡ ምንተኒ ፡ እምደም ፡ አወርድ መዓትየ ፡ ላዕለ ፡ ይእቲ ፡ ነፍስ ፡ እንተ ፡ በልዓት ፡ ደመ ፡ ወእደመስሳ ፡ እምሕዝባ ።

፩ሺ፰፻፸፮ ኢትክሥት ፡ ኀፍረተ ፡ እምከ ፡ ወኢ ፡ ኀፍረተ፡ ብእሲተ ፡ እቡከ ፡ አው ፡ ኀፍረተ ፡ እኅትከ ፡ ወወለተ ፡ ወልድከ ፡ ወወለተ ፡ ወለትከ ፡ ወኀፍረተ ፡ ወለታ ፡ ለብእሲተ ፡ እቡከ ፡ ወእኅተ ፡ አቡከ ። ወእኅታ ፡ ለእምከ ፡ ወብእሲተ ፡ እኅው ፡ አቡከ ፡ ወብእሲተ ፡ እኁከ ፡ ወብእሲተ ፡ ወልድከ ፡ ወብእሲተ ፡ ወልዳ ። ወከማሁ ፡ ወለተ ፡ ወልዳ ፡ ወወለተ ፡ ወለታ ፡ ወብእሲተኒ፡ ምስለ ፡ እኅታ ፡ እንተ ፡ ሀለወት ፡ በሕይወታ ፡ ወብእሲተኒ ፡ በጊዜ ፡ ተክቶሃ ፡ ወኢትርኩስ ፡ በብእሲተ ፡ ካልእከ ። ወተባዕትኒ ፡ ኢይስክብ ፡ ምስለ ፡ ተባዕት ፡ ከመ ፡ ሰኪበ ፡ አንስት ፡ ወኢ.ይርኩሱ ፡ ብእሲ ፡ ወኢ ፡ ብእሲት ፡ በምንትኒ ፡ እምእንስሳ ።

፩ሺ፰፻፸፯ ወእመ ፡ ተዓጽዱ ፡ እክለ ፡ ማእረርክሙ ፡

ስለ ፡ ብሉይና ፡ ሐዲስ ።

፩ሺ፰፻፸፬ እግዚአብሔር ፡ ከከለከለው ፡ ወገን ፡ ሊሠርዋት ፡ በማይገባ ፡ በአንዲት ፡ ሥራ ፡ የበደለ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ባያውቅም ፡ ቍርባን ፡ ያቅርብ ። ዘሌ ፡ ፭ ፡ ፲፯ - ፲፰) ። አንዱም ፡ ባልጀራውን ፡ አደራ ፡ በማስቀመጥ ፡ ወይም ፡ በሥራ ፡ ስምምነት ፡ ቢከዳው ፡ ወይም ፡ ጓደኛውን ፡ የሚያስቆጣው ፡ ወይም ፡ የሚበድለው ፡ ወይም ፡ የጠፋችውን ፡ ወይም ፡ የኮበለለችውን ፡ አግኝቶ ፡ እርሱዋን ፡ ቢክድ ፡ ሰው ፡ ከሚሠራቸው ፡ ከእንዚህ ፡ ሁሉ ፡ በእንዲቱ ፡ የማለ ፡ በእርሱዋም ፡ የበደለ ፡ ከበደለም ፡ በኋላ ፡ የቀማውን ፡ ይመልስ ። የሰረቀውንም ፡ ወይም ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ያስቀመጡበትን ፡ አደራ ፡ ወይም ፡ የጠፋችውን፡ ወይም፡ የኮበለለችውን፡ ያገኘ፡ ወይም፡ በሐሰት ፡ የማለበትን ፡ ነገር ፡ ቢሆን ፡ ይመልስ ። በእርሱም ፡ ላይ ፡ እምስት ፡ እድርጎ ፡ ይጨምር ። ለእርሱም ፡ ለሆነው ፡ (ለባለገንዘቡ) ፡ በተከራከረበት ፡ ወይም ፡ በደሉን ፡ ባመነበት ፡ ቀን ፡ ይስጠው ። ቍርባንም ፡ ያቅርብ ። (ዘሌ ፡ ፮ ፡ ፩ -፮) ።

፩ሺ፰፻፸፭ ከእስራኤል ፡ ጀልች ፡ ወይም ፡ ከ..ካከላቸው፡ ከሚኖሩ ፡ ልዩ ፡ ወገኖች ፡ ከደም ፡ ወገን ፡ ምንም ፡ ምን ፡ የሚበላ ፡ ቢኖር ፡ ደም ፡ በበላች ፡ ሰውነት ፡ ላይ ፡ መዓቴን ፡ አወርዳለሁ ። ከወገኗም ፡ ለይቼ ፡ እጠፋታለሁ ። ( ዘሌ ፡ ፲፯ ፡ ፲ - ፲፭ ) ።

፩ሺ፰፻፸፮ የእናትህን ፡ ኀፍረት ፡ አትግለጽ ። የአባትህን ፡ ሚስት ፡ ኀፍረትም ፡ የእኅትህንም ፡ ኀፍረት ፡ የወንድ ፡ ልጅህን ፡ ሴት ፡ ልጅም ፡ የሴት፡ ልጅህን ፡ ሴት ፡ ልጅም ፡ የአባትህን ፡ የሚስት፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ኀፍረትም ፡ የአባትህንም ፡ እኅት ፡ የእናትህን ፡ እኅት ፡ የአባትህን ፡ የወንድም ፡ ሚስት ፡ የወንድምህን ፡ ሚስት ፡ የልጅዋንም ፡ ሚስት ፡ እንደዚሁም ፡ የወንድ ፡ ልጅዋን ፡ ሴት ልጅ ፡ የሴት ፡ ልጅዋንም ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ሴትንም ፡ ከልጅዋ ፡ ጋራ ፡ በሕይወት ፡ ሳለች ፡ ሴትንም ፡ በግዳጅዋ ፡ ጊዜ ፡ በጓደኛህም ፡ ሚስት ፡ አትርከስ ። ሴተን ፡ እንደመተኛትም ፡ ወንድ ፡ ከወንድ ፡ ጋራ ፡ አይተኛ ። ወንድ ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ከእንበሳ ፡ ወገን ፡ በማናቸውም ፡ አይርከሱ። (ዘሌ ፡ ፲፰ ፡ ፮ - ፳፫) ።

፩ሺ፰፻፸፯ የአዝመራችሁን ፡ እህል ፡ በምታጭዱበት ፡

አንቀጽ ፡ ሣኛ ።

ኢትጠናቀቁ ፡ ዕጺደ ፡ እንዘ ፡ ተዐጽዱ ፡ ወኢት እሪ ፡ ዘወድቀ ፡ እምኔሁ ፡ ወኢትግባእ ፡ እምድኅረ ፡ ቀሲመ ፡ ዓጸደ ፡ ወይንከ ፡ ወኢትእሪ ፡ ዘተርፈ ፡ እላ ፡ ኅድጎ ፡ ለነዳይ ፡ ወለግዩር ።

፩ሺ.፰፻፹፫ ወእነ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክክሙ ፡ እፈድየክሙ ፡ ሠናየ ፡ ወኢታቢት ፡ ዓስበ ፡ ለዓሳብ፡ በኀቤከ ፡ እስከ ፡ ይጸብሕ ፡ ወኢትንብብ ፡ ሕሡመ ፡ ላዕለ ፡ ጽሙም ፡ ወኢትደይ ፡ ዕቅፍተ ፡ ቅድመ ፡ ዕዉር ፡ ወኢትጠየር ፡ በያፍ ፡ ወኢትትፋለሱ ።

፩ሺ.፰፻፹፬ ወኢትግበሩ ፡ ቈናዝዓተ ፡ እምሥዕርተ ፡ ርእስክሙ ፡ ወኢትላጺ ፡ መንፈቀ ፡ ሥዕርተ ፡ ርእስከ ፡ ወኢትላጽዩ ፡ ስፍሐ ፡ ጽሕምክሙ ። ወእመቦ ፡ ዘሞተ ፡ ኢተሐንፍጡ ፡ ገጸክሙ ፡ ወመላጼ ፡ ኢታቅርቡ ፡ ዲበ ፡ ሥጋክሙ ፡ ወኢትኅትሙ ፡ እባለክሙ ፡ በመርፍዕ ። ወኢታዘምዋ ፡ ለወለትከ ፡ ወኢትሑር ፡ ኀበ ፡ ሰብእ ፡ ሐረስ ፡ ወተአማርያን ፡ ወኢትትልውዎሙ ፡ ለሰብእ ፡ ሥራይ ፡ እስመ ፡ እነ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክክሙ ፡ ዘአስምር ፡ ኅቡአ ።

፩ሺ.፰፻፹፭ ወአክብር ፡ ለዘይልህቅ ፡ እምኔከ ፡ ወኢታሕሥሞ ፡ ላዕለ ፡ ግዩር ፡ ዘየኀድር ፡ ውስተ ፡ ምድርክሙ ፡ ወይኩን ፡ ማእከሌክሙ ፡ ከመ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔክሙ ። ወኢትግበሩ ፡ ዐመፃ ፡ በውስተ ፡ ፍትሕ ፡ ወኢ ፡ በውስተ ፡ ምግባር ፡ ዘኍልቍ ፡ ወኢ ፡ በመዳልው ፡ ወኢ ፡ በመስፈርት ፡ እላ ፡ መዳልውክኒ ፡ ዘበጽድቅ ፡ ይኩና ፡ ወእእባነ ፡ መዳልውክኒ ፡ ዘበጽድቅ ፡ ይኩና ፡ ወመስፈርትክኒ ፡ ወኀሞርክኒ ፡ ዘበጽድቅ ፡ ይኩንክሙ ፡ እስመ ፡ ራትዕ ፡ እነ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምላክክሙ ።

፩ሺ.፰፻፹፮ ወዘይከው ፡ ዘርእ ፡ ውስተ ፡ ብእሲት ፡ ንክርት ፡ ዘኢማእምንት ፡ ይትወገር ፡ በእብን ፡ ወዘተዐወረ ፡ ኪያሁ ፡ እነ ፡ እደመስሶ ።

፩ሺ.፰፻፹፯ ዘማዊ ፡ ወዘማዊት ፡ ይትቀተሉ ፡ ከማሁ ዘይረክቦ ፡ በእንስሳ ፡ ብእሲሁ ፡ ይትቀተል ፡ ወእንስሳሁ ፡ ይትወገር ፡ መሠርይ ፡ ወተአማኒ ይትቀተሉ ። ወኢታውስብ ፡ ብእሲተ ፡ ዘማዊተ ፡ ወኢ ፡ እንተ ፡ ደኀርዋ ። ወለተ ፡ ካህን ፡ ለእመ ፡ ዘመወት ፡ እስመ ፡ አስተኃፈ

ስለ ፡ ብሉይና ፡ ሐዲስ ።

ጊዜ ፡ ስታጭዱ ፡ ማጨድን ፡ አትጠናቀቁ ። (እዋርታችሁ ፡ አትጨዱ) ፡ ከእርሱ ፡ የወደቀውንም ፡ አትልቀም ። ወይንህንም ፡ ከለቀምህ ፡ በኋላ ፡ አትመለስ ። የተረፈውንም ፡ አትልቀም ። ለደኃና ፡ ለስደተኛ ፡ ተወው ፡ እንጂ ። ዘዳ ፡ ፳፬ ፡ ፲፱ - ፳፪) ።

፩ሺ.፰፻፹፫ እኔ ፡ ፈጣሪያችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልካሙን ፡ እከፍላችኋለሁ ። የምንደኛን ፡ ደመወዝ ፡ እስኪነጋ ፡ ድረስ ፡ በአንተ ፡ ዘንድ ፡ አታሳድር ። በደንቆሮ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አትናገር ። በዕውር ፡ ፊት ፡ እንቅፋት ፡ አትጨምር ። በያፋም ፡ አታማርት ። አትዘሩም ።

፩ሺ.፰፻፹፬ ከራሳችሁ ፡ ፀጕር ፡ ብርንጎ ፡ አትሥሩ ። የራስ ፡ ፀጕርህን ፡ እኩሌታ ፡ አትላጭ ። የ ጢማችሁንም ፡ ስፋት ፡ አትላጩ ። የሞተም ፡ ቢኖር ፡ ፊታችሁን ፡ አትንጩ ። ወደ ፡ ሥጋችሁም ፡ ምላጭ ፡ አታቅርቡ ። ሰውነታችሁንም ፡ በመርፌ ፡ አትነቀሱ ። ሴት ፡ ልጅህን ፡ አመንዝራ ፡ አታድርጋት ። ወደቀንቃኞች ፡ ሰዎችና ፡ ወደባለአምልኮቶች ፡ አትሂዱ ። የሥራይ ፡ ሰዎችን ፡ (ሥራይ ፡ የሚያደርጉ ፡ ሰዎችን) ፡ አትከተላቸው ። የተሰወረውን ፡ የማውቅ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጣሪያችሁ ፡ ነኝና ።

፩ሺ.፰፻፹፭ ከአንተ ፡ የሚሽመግለውንም ፡ አክብረው ። በሀገራችሁ ፡ በሚኖር ፡ መጻተኛ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አታድርጉ ። በመካከላችሁም ፡ ከእናንተ ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ይሁን ። በፍርድ ፡ ወይም ፡ በቍጥር ፡ ልክ ፡ በሚዛን ፡ ወይም ፡ በመሥፈሪያ ፡ ዓመፅን ፡ አታድርጉ ። ሚዛኖችህ ፡ በእውነት ፡ ይሁኑ ፡ እንጂ ። የሚዛንህ ፡ (የምትመዝን ባቸው) ፡ ድንጋዮችም ፡ በእውነት ፡ ይሁኑ ። መስፈሪያህና ፡ ኅሞርህም ፡ በእውነት ፡ ይሁንላችሁ ። እኔ ፡ ፈጣሪያችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅን ፡ ነኝና ። (ዘሌ ፡ ፲፱ ፡ ፱ - ፴፯) ።

፩ሺ.፰፻፹፮ በአላመነች ፡ በባዕድ ፡ ሴት ፡ ውስጥ ፡ ዘርዕ ፡ ያፈሰሰ ፡ በደንጋይ ፡ ይወገር ። እርሱንም ፡ ቸል ፡ ያለውን ፡ እኔ ፡ አጠፋዋለሁ ። (ዘሌ ፡ ፳ ፡ ፱) ።

፩ሺ.፰፻፹፯ ዘማዊና ፡ ዘማዊት ፡ (አመንዝራና ፡ አመንዝራዪት) ፡ ይገደሉ ። እንደዚሁም ፡ በከብት ፡ የረከበ ፡ በውየው ፡ ይገደል ። እንስሳውም ፡ ይወገር ። መሠርይ ፡ በእርሱም ፡ የሚያምን ይገደሉ ። ( ዘሌ ፡ ፳ ፡ ፲ ፡ ፲፩ ፡ ፳፯ ) ። አመንዝራዪቱን ፡ ወይም ፡ የፈቷትን ፡ ሴት ፡ አታግባ ። የካ

ረቶ ፡ ለእቡሃ ፡ ያውዕዮዋ ፡ በእሳት ።

፩ሺ፭፻፺፰ ወካህን ፡ ዘየዐቢ ፡ ኢይንጺ ፡ ሥዕርቶ ፡ ወኢይሥጥጥ ፡ አልባሲሁ ፡ ላዕለ ፡ ዘሞተ ፡ ወኢያውስብ ፡ ዘአንበለ ፡ ድንግል ፡ እንተ ፡ እምነገዱ።

፩ሺ፭፻፺፱ ወመበለቶስ ፡ አው ፡ እንተ ፡ ደኅርዋ ፡ እው ፡ እንተ ፡ ዘመወት ፡ ኢያውስብ ፡ አሐተ ፡ አምኔሆን ።

፩ሺ፭፻ ፯ ወዘሂ ፡ ቀርበ ፡ ኀበ ፡ ቅድሳት ፡ እንዘ ፡ ርኩስ ፡ ውእቱ ፡ ትሠረው ፡ ይእቲ ፡ ነፍስ ፡ እምኀቤየ ። ወኵሉ ፡ ዘእምባዕድ ፡ ዘመድ ፡ ኢይብላዕ ፡ እምቅድሳት ፡ እስከ ፡ ፈላሲሁ ፡ ለካህን ፡ ወዓሳቡ ።

፩ሺ፭፻ ፯፩ ወዘሰ ፡ አጥረየ ፡ ካህን ፡ በንዋዩ ፡ ወዘሂ ፡ ተወልደ ፡ በቤቱ ፡ ይብልዑ ፡ እመባልዕቲሁ ። ወወለተ ፡ ብእሲ ፡ ካህን ፡ ለእመ ፡ አውሰበት ፡ ብእሴ ፡ እምካልእ ፡ ዘመድ ፡ ኢትብላዕ ፡ እምዓሥራት ፡ ዘቅድሳት ።

፩ሺ፭፻ ፯፪ ወዘቦ ፡ ነውር ፡ ላዕሌሁ ፡ ኢታምጽኡ ፡ መባአ ፡ እስመ ፡ ኢይሠጠወከሙ ፡ ወኵሎ ፡ ዓሥራተ ፡ አልሕምት ፡ ወአባግዕ ፡ ይኩን ፡ ዓሥራየ ፡ ቅዱስ ፡ ለእግዚአብሔር ።

፩ሺ፭፻ ፯፫ ትዳ ፡ ወነበቦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሙሴ ፡ወይቤሎ ፡ በሎሙ ፡ ለካህናት ፡ ይባርክዎሙ ፡ ለሕዝብ ፡ እንዘ ፡ ይቤሉ ፡ "ለይባርከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወይዕቀብከ ፡ ወያብርህ ፡ ገጾ ፡ ላዕሌከ ፡ ወይምሐርከ ፡ ወይሚም ፡ ፈቃዶ ፡ ኀቤከ ፡ ወየሀብከ ፡ ሰላመ ።" ወይበሉ ፡ በስምየ ፡ ላዕለ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ወአነሂ ፡ እባርኮ ፡ ላዕሌሆሙ ።

፩ሺ፭፻ ፯፬ ትሔ ፡ ወኢታንቀልቅል ፡ እምነ ፡ ትእዛዝ ፡ ዘነገሩከ ፡ መኳንንት ፡ ኢ ፡ ለየማን ፡ ወኢ ፡ ለፀጋም ። ወኢታቅም ፡ ፩ደ ፡ ስማዕተ ፡ ላዕለ ፡ ብእሲ ፡ በምንትኒ ፡ ግብር ፡ እምአበሳ ፡ ወስሕተት ፡ አላ ፡ በስምዐ ፡ ፪ቱ ፡ ወ፫ቱ ፡ ይቀውም ፡ ኵሉ ፡ ነገር ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ስምዐ ፡ ፩ዱ ፡ በዐመፃ ፡ ላዕለ ፡ ብእሲ ፡ ለይትኃሠሡ ፡ መኳንንት ፡ ፈድፋደ ፡ ወይግበሩ ፡ ቦቱ ፡ በከመ ፡ ፈተየ ፡ ይደግበር ፡ ላዕለ ፡ ካልኡ ።

፩ሺ፭፻ ፯፭ ወአግብእ ፡ ዘጕየ ፡ አምኀበ ፡ እኁከ ፡ ወለእመ ፡ ኢኮነ ፡ እምአዝማዲከ ፡ እው ፡ ዘኢተአ



ሀን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ብትሰስን ፡ አባቷን ፡ አሳፍራዋለችና ፡ በአሳት ፡ ያቃጥሉዋት ።

፩ሺ፭፻፺፰ ታላቁ ፡ ካህን ፡ ለሞተ ፡ ሰው ፡ ጠጉሩን ፡ አይንጭ ። ልብሱንም ፡ አይቅደድ ። ከነገዱ ፡ ከሆነች ፡ ድንግል ፡ በቀር ፡ አያግባ ።

፩ሺ፭፻፺፱ ባል ፡ የሌላትን ፡ ወይም ፡ የፈቷትን ፡ ወይም ፡ የሰሰነችውን ፡ ከእነዚህ ፡ አንዲቱን ፡ አያግባ ። (ዘሌ ፡ ፳፮ ፡ ፮ - ፲፭) ።

፩ሺ፭፻ ፯ ርኩስ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ወደ ፡ ተቀደሰው ፡ የቀረበው ፡ ሰው ፡ ነፍስ ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ትጥፋ ። እስከ ፡ ካህኑ ፡ መጻተኛ ፡ እስከ ፡ ምንደኛው ፡ ድረስ ፡ ከሌላ ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ ከመሥዋዕት ፡ አይብላ ።

፩ሺ፭፻ ፯፩ ካህን ፡ በገንዘቡ ፡ የገዛው ፡ በቤቱም ፡ የተወለደው ፡ ከሚባለው ፡ (ከመሥዋዕቱ) ፡ ይብሉ ። የካህኑ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ከሌላ ፡ ወገን ፡ የሆነ ፡ ባል ፡ ብታገባ ፡ ለመሥዋዕት ፡ ከሚሆነው ፡ አሥራት ፡ አትብላ ። (ዘሌ ፡ ፳፪ ፡ ፫ - ፲፩ ።

፩ሺ፭፻ ፯፪ ነውር ፡ በላዩ ፡ ያለበትን ፡ መባዕ ፡ እድርጋችሁ ፡ አታምጡ ። አልቀበላችሁምና ። የላሞችና ፡ የበጎች ፡ አሥራት ፡ ሁሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተለየ ፡ አሥራት ፡ ይሁን ። (ዘሌ ፡ ፳፪ ፡ ፲፰ - ፳፭) ።

፩ሺ፭፻ ፯፫ ትዳ ። እግዚአብሔርም ፡ ለሙሴ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ነገረው ። ሕዝቡን ፡ እንዲህ ፡ እያሉ ፡ ይመርቋቸው ፡ ዘንድ ፡ ለካህናት ፡ ንገራቸው ። እግዚአብሔር ፡ ይባርከህ ፡ ይጠብቅህም ። ፊቱንም ፡ ያብራልህ ። ይቅርም ፡ ይበልህ ። ፈቃዱንም ፡ በአንተ ፡ ያሳድር ። ሰላሙንም ፡ ይስጥህ ። በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ስሜን ፡ ይናገሩ ። እኔም ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ እባርካለሁ ። (ዘኍ ፡ ፮ ፡ ፳፬ - ፳፯) ።

፩ሺ፭፻ ፯፬ ትሄ ። መኳንንት ፡ ከነገሩህ ፡ ትእዛዝ ፡ ወደ ቀኝ ፡ ወይም ፡ ወደግራ ፡ አትናወጥ ። ከበደልና፡ ከስሕተት ፡ ወገን ፡ በማናቸውም ፡ ሥራ ፡ በሰው ላይ ፡ አንድ ፡ ምስክር ፡ አትጥራ ። ነገር ፡ ሁሉ ፡ በ፪ና ፡ በ፫ ፡ ምስክር ፡ ይጽና ፡ እንጂ ። አንድ ፡ ሰው ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ በዓመፅ ፡ (በሐሰት) ፡ ምስክር ፡ ቢሆን ፡ ዳኞች ፡ በጥብቅ ፡ መርምረው ፡ በሌላው ፡ ሊያደርግ ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡ በእርሱ ፡ ያድርጉ ። (ዘዳ ፡ ፲፱ ፡ ፲፩ - ፳) ።

፩ሺ፭፻ ፯፭ ከወንድምህ ፡ የጠፋውን ፡ መልስለት ። ከዘመዶችህም ፡ ወገን ፡ ባይሆን ፡ ወይም ፡ የማታ

አንቀጽ ፡ ፵፭ ።

ምሮ ፡ እንብሮ ፡ ኀበ ፡ ማኅደርከ ፡ ወየሀሉ ፡ ኀቤከ ፡ እስከ ፡ የኀሥሥ ፡ እኁከ ፡ ወታገብእ ፡ ኀቤሁ ፡ እንስሳሁ ፡ ወልብሶ ። ወለዙሉ ፡ ጕያዪ ኢይደልወከ ፡ ከመ ፡ ትትዐወር ፡ በእንቲአሁ ።

፩ሺ፭፻፺፮ ኢይልበስ ፡ እደው ፡ አርእያ ፡ አንስት ፡ ወአንስትኒ ፡ ኢይልበሳ ፡ አርእያ ፡ እደው ፡ ወኢየሀሉ ፡ ሥርዓተ ፡ እደው ፡ ላዕለ ፡ አንስት ፡ ወኢሥርዓተ ፡ አንስት ፡ ላዕለ ፡ እደው ፡ እስመ ፡ ርኩስ ፡ ውእቱ ፡ ዝንቱ ።

፩ሺ፭፻፺፯ ግበር ፡ ተሥላስ ፡ ሐዑር ፡ በቤትከ ፡ ወኢትኅድግ ፡ መካነ ፡ ዘይወድቀከ ፡ እምኔሁ ።

፩ሺ፭፻፺፰ ወለእመ ፡ ተረክበ ፡ ብእሲ ፡ ዘናሁ ፡ ሰረቀ ፡ ነፍሰ ፡ እምአኃዊሁ ፡ ወቀነዮ ፡ እው ፡ ሤጦ ፡ ቅትሎ ፡ ለሰራቂ ።

፩ሺ፭፻፺፱ ወእምከመ ፡ ኮነ ፡ ተጻልአ ፡ ማእከለ ፡ ሰብእ ፡ ያምጽእዎሙ ፡ ኀበ ፡ መኳንንት ፡ ከመ ፡ ይፍትሑ ፡ ማእከሌሆሙ ፡ ወያጸድቅዎ ፡ ለጻድቅ ፡ ወየዐምፅዎ ፡ ለዐማፂ ።

፩ሺ፮፻ ወለእመ ፡ ይደልዎ ፡ ለዓማፂ ፡ ቅሥፈት ፡ ያሰክብዎ ፡ በከብዱ ፡ ወይቅሥፎ ፡ በቅድሜሁ ፡ በእምጣነ ፡ ኃጢአቱ ፡ ይቅሥፎ ፡ በኍልቈ ፡ ፵ ፡ ወኢይወስኩ ፡ ላዕሌሁ ፡ ምንትኒ ።

፩ሺ፮፻፩ ወኢትፈፅሞ ፡ አፉሁ ፡ ለላህም ፡ ሶበ ፡ ታከይድ ፡ እክለ ።

፩ሺ፮፻፪ ወዳግማዊስ ፡ ሕግ ፡ ቦ ፡ እምኔሁ ፡ ዘያኤምር ፡ ኀበ ፡ ልዑላን ፡ ኀበ ፡ ኅርየተ ፡ ፈቃዱ ፡ ለዘይፈቅድ ፡ ይኩን ፡ ፍጹመ ፡ ዘከመ ፡ ዐቂበ ፡ ድንግልና ፡ በከመ ፡ ተነግረ ፡ በእንቀጸ ፡ ተዋስቦ ። ወዘከመ ፡ ኀዲገ ፡ ንዋይ ፡ ወመንኖተ ፡ ፍጹመ ፡ ወኀዲገ ፡ ዓለም ፡ ወተሊወ ፡ ክርስቶስ ፡ ወምግባራቲሁ ፡ በእምጣነ ፡ ኀይሉ ፡ ለሥጋዊ ፡ በከመ ተነግረ ፡ በእንቀጸ ፡ መነኰሳት ።

፩ሺ፮፻፫ ወእምኔሁ ፡ ዘተነግረ ፡ ትእዛዙ ፡ ፍጹመ ፡ ዘከመ ፡ ገሥጾተ ፡ ኀይለ ፡ መዓት ፡ ወኀይለ ፡ ፍትወት ፡ ወእሠንዮ ፡ ለዘእሡንየ ፡ ወለዘእሕሡሚ ፡ ወኀዲገ ፡ አድልዎ ፡ ውስተ ፡ እምልከ ፡ በምጽዋት ፡ ወጸሎት ፡ ወጾም ፡ ውኑኒሀ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ህየንተ ፡ ካልእኒሁ ፡ ወምግሮተ ፡ ሰብእ ፡ ምግባረ ፡ ትሩፋት ፡ ወገቢሮ ፡

ስለ ፡ ብሉይና ፡ ሐዲስ ።

ውቀው ፡ ቢሆን ፡ በቤትህ ፡ አኑረው ። ወንድምህ ፡ እስኪፈልገው ፡ ድረስ ፡ በአንተ ፡ ዘንድ ፡ ይኑር ። እንስሳውንና ፡ ልብሱንም ፡ ትመልስለታለህ ። ስለ ፡ ኮብላይም ፡ ሁሉ ፡ ቸል ፡ ልትል ፡ አይገባህም ።

፩ሺ፭፻፺፮ ወንዶች ፡ እንደ ፡ ሴቶች ፡ አይልበሱ ። ሴቶችም ፡ እንደ ፡ ወንዶች ፡ አይልበሱ ። የወንዶች ፡ ሥርዓት ፡ በሴቶች ፡ ላይ ፡ የሴቶችም ፡ ሥርዓት ፡ በወንዶች ፡ ላይ ፡ አይኑር ። ይህ ፡ ርኩስ ፡ ነውና ። (ዘዳ ፡ ፳፪ ፡ ፩ - ፭) ።

፩ሺ፭፻፺፯ በቤትህ ፡ ፫ ፡ ደረጃ ፡ አብጅ ። (፫ ፡ ቅጥር ፡ አብጅ) ፡ ከእርሱም ፡ የሚጥልህን ፡ ቦታ ፡ አትተው ። (ዘዳ ፡ ፳፪ - ፰) ።

፩ሺ፭፻፺፰ ከወንድሞቹ ፡ ወገን ፡ እነሆ ፡ ነፍስ ፡ የሰረቀ ፡ የገዛትም ፡ ወይም ፡ የሸጣት ፡ ሰው ፡ ቢገኝ ፡ ሌባውን ፡ ግደለው ። (ዘዳ ፡ ፳፬ ፡ ፯) ።

፩ሺ፭፻፺፱ በሰዎች ፡ መካከል ፡ ጠብ ፡ ቢሆን ፡ በመካከላቸው ፡ ይፈርዱ ፡ ዘንድ ፡ ወደዳኞች ፡ ያምጧቸው ። እውነተኛውን ፡ እውነተኛ ፡ ነህ ፡ ይበሉት ። በደለኛውንም ፡ በደለኛ ፡ ነህ ፡ ይበሉት ።

፩ሺ፮፻ ለዓመፀኛም ፡ ግርፋት ፡ ቢገባው ፡ በሆዱ ፡ ያስተኙት ። በፊቱም ፡ ይግረፈው ። በኃጢአቱ ፡ ልክ ፡ አርባ ፡ ቍጥር ፡ ይግረፈው ። ከአርባ ፡ በላይ ፡ ምንም ፡ አይጨምሩ ።

፩ሺ፮፻፩ እህል ፡ በምታበራይ ፡ ጊዜ ፡ የበሬውን ፡ አፍ ፡ አታፍን ። (ዘዳ ፡ ፳፭ ፡ ፩ - ፭) ።

፩ሺ፮፻፪ ሁለተኛው ፡ ሕግ ፡ ግን ፡ ፍጹም ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ የሚወድ ፡ ሰው ፡ ወደሚሻው ፡ ምርጫ ፡ ወደ ፡ ከፍተኞች ፡ የሚያመለክት ፡ ከእርሱ ፡ ወገን ፡ አለ ። ይኸውም ፡ በጋብቻ ፡ አንቀጽ ፡ እንደተነገረ ፡ ድንግልናን ፡ እንደመጠበቅ ፡ ገንዘብንም ፡ እንደመተውና ፡ ፈጽሞ ፡ እንደመናቅ ዓለምንም ፡ ትቶ ፡ ክርስቶስንና ፡ ሥራዎቹን ፡ በሥጋዊ ፡ ተፈጥሮ ፡ ኃይል ፡ ልክ ፡ እንደመከተል ፡ ያለ ፡ ነው ። በእንቀጸ ፡ መነኰሳት ፡ እንደ ተነገረ ። (ፍ ፡ ነ ፡ ፫፻፵፬ ። ፳፻፴) ።

፩ሺ፮፻፫ ከእርሱም ፡ ፈጽሞ ፡ የተነገረ ፡ ትእዛዙ ፡ የቁጣን ፡ ኀይልና ፡ የፍትወትን ፡ ኀይል ፡ እንደ ፡ መግታት ፡ ነው ። መልካም ፡ ለአደረገና ፡ ክፋም ፡ ለአደረገ ፡ መልካም ፡ ማድረግ ፡ በእምልኮ ፡ በምጽዋትና ፡ በጸሎት ፡ በጾምም ፡ ጊዜ ፡ አድልዎን ፡ መተው ፡ ስለሌላዎቹም ፡ ፈንታ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ መሻት ፡ ለሰዎችም ፡

በቅድሜሁ ፡ ወትስማሥት ፡ ላዕለ ፡ ምንዳቤ ፡ በሐዊረ ፡ ፍኖት ፡ እንተ ፡ ታበጽሕ ፡ ውስተ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ። ወተነግሎ ፡ ላዕለ ፡ ተቀትሎ ፡ በእንበለ ፡ ግዚእ ፡ እምሃይማኖተ ፡ ጽድቅ ፡ በከመ ፡ ተነግረ ፡ በአንቀጸ ፡ ሰማዕታት

፩ሺ፮፻፬ ቃለ ፡ ወንጌል ፡ ዘእማቴዎስ ፡ ወንጌላዊ ፡ በእንተ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ሰብሐት ፡ ዘ፭ቱ ፡ ወሶበ ፡ ርእየ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ብዙኃነ ፡ አሕዛበ ፡ ዐርገ ፡ ውስተ ፡ ደብር ፡ ወነበረ ፡ ወመጽኡ ፡ አርዳኢሁ ፡ ኀቤሁ ፡ ወከሠተ ፡ አፉሁ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ወመሀሮሙ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ብፁዓን ፡ ነዳያን ፡ በመንፈስ ፡ እስመ ፡ ሎሙ ፡ ይእቲ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ። ብፁዓን ፡ እለ ፡ ይላሕዉ ፡ ይእዜ ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ይትፌሥሑ ። ብፁዓን ፡ ትሑታን ፡ እስመ እሙንቱ ፡ ይወርስዋ ፡ ለምድር ። ብፁዓን ፡ እለ ፡ ይርኅቡ ፡ ወይጸምኡ ፡ በእንተ ፡ ጽድቅ ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ይጸግቡ ። ብፁዓን ፡ መሐርያን ፡ እስመ ፡ ሎሙኒ ፡ ይምሕርዎሙ ። ብፁዓን ፡ ንጹሓነ ፡ ልብ ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ይሬእይዎ ፡ ለእግዚአብሔር ። ብፁዓን ፡ ገባርያነ ፡ ሰላም ፡ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ውሉደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሰመዩ ። ብፁዓን ፡ እለ ፡ ይሰደዱ ፡ በእንተ ፡ ጽድቅ ፡ እስመ ፡ ሎሙ ፡ ይእቲ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ። ብፁዓን ፡ አንትሙ ፡ ሶበ ፡ ይሰድዱክሙ ፡ ወይጼእሉክሙ ፡ ወይዘነጕጉክሙ ፡ ወይነቡ ፡ ኵሎ ፡ እኩየ ፡ በላዕሌክሙ ፡ እንዘ ፡ ይሔስዉ ፡ ዲቤክሙ ፡ በእንቲአየ ፡ ተፈሥሑ ፡ ወተኃሠዩ ፡ እስመ ፡ ዐስብክሙ ፡ ዐቢይ ፡ በሰማያት ፡ እስመ ፡ ከማሁ ፡ ሰደድዎሙ ፡ ለነቢያት ፡ እለ ፡ እምቅድሜክሙ ። ይብራህ ፡ ብርሃንክሙ፡ በቅድመ ፡ ሰብእ ፡ ከመ ፡ ይርእዩ ፡ ምግባሪክሙ ፡ ሠናየ ፡ ወይሰብሕዎ ፡ ለአቡክሙ ፡ ዘበሰማያት ። ወዘሰ ፡ ይገብር ፡ ወይሜህር ፡ ዐቢየ ፡ ይሰመይ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ። እብለክሙ ለእመ ፡ ኢያፈድፈድክሙ ፡ ጻዲቀ ፡ እምጸሐፍት ፡ ወፈሪሳውያን ፡ ኢትበውኡ ፡ ውስተ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ።"

፩ሺ፮፻፭ ዘሀቱ ፡ ሰማዕክሙ ፡ ዘተብህለ ፡ ለቀደምት ፡ ክሙ ፡ ኢትቅትል ፡ ነፍሰ ፡ ወለዘቀተለ ፡ ነፍሰ ፡ ይደሉ ፡ ላዕሌሁ ፡ ኵነኔ ። ወእንሰ ፡ እብለክሙ ፡



የትሩፋትን ፡ ሥራ ፡ ማስተማር ፡ በፊቱም ፡ እርሱዋን ፡ መሥራት ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የምታደርስ ፡ መንገድን ፡ በመሄድ ፡ ጊዜ ፡ በችግር ፡ ላይ ፡ መታገሥ ፡ በአንቀጸ ፡ ሰማዕት ፡ እንደተነገረ ፡ ከእውነተኛው ፡ ሃይማኖት ፡ ባለ መመለስ ፡ ለመሞት ፡ መጨከን ፡ ነው ። (ፍ ፡ ነ ፡ ፳፻፰፩) ።

፩ሺ፮፻፬ ምስጋና ፡ ይግባውና ፡ ስለጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ማቴዎስ ፡ ከጻፈው ፡ የወንጌል ፡ ቃል ፡ ፭ ። ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ከተራራ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ ተቀመጠ ። ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ወደእርሱ ፡ መጡ ። ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ ነገሩን ፡ ጀመረ ። እንዲህም ፡ እያለ ፡ አስተማራቸው ። በመንፈስ ፡ ድሆች ፡ የሆኑ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ። መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የእነርሱ ፡ ናትና ። ዛሬ ፡ የሚያለቅሱ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ። ደስ ፡ ይላቸዋልና ። ትሑታን ብፁዓን ፡ ናቸው ። እነርሱ ፡ ምድርን ፡ ይወርሱዋታልና ። ስለ ፡ ጽድቅ ፡ የሚራቡና ፡ የሚጠሙ ብፁዓን ፡ ናቸው ። እነርሱ ፡ ይጠግባሉና ። ይቅር ፡ የሚሉ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ። እነርሱንም ፡ ይቅር ፡ ይሏቸዋልና ። ልበ ፡ ንጹሖች ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ። እነርሱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያዩታልና ። ሰላምን ፡ የሚያደርጉ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ። እነርሱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ይባላሉና ። ስለ፡ ጽድቅ ፡ የሚሰደዱ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ። መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የእነርሱ ፡ ናትና ። ቢያሳድዱዋችሁ ፡ ቢሰድቡዋችሁ ፡ ቢነቅፉዋችሁ ፡ ስለእኔም ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ እየዋሹ ፡ በላያችሁ ፡ ክፉን ፡ ሁሉ ፡ ቢናገሩም ፡ ብፁዓን ፡ ናችሁ ። ዋጋችሁም ፡ በሰማያት ፡ ታላቅ ፡ ነውና ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ። ከእናንተ ፡ አስቀድሞ ፡ የነበሩ ፡ ነቢያትን ፡ እንደዚሁ ፡ አሳድደዋቸዋልና ። ብርሃናችሁ ፡ በሰዎች ፡ ፊት ፡ ይብራ ። ሥራችሁን ፡ አይተው ፡ በሰማያት ፡ ያለ ፡ አባታችሁን ፡ ያመሰግኑት ፡ ዘንድ ። የሚሠራ ፡ ግን ፡ የሚያስተምርም ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ታላቅ ፡ ይባላል ። ከጸሐፍትና ፡ ከፈሪሳውያን ፡ ጽድቅን ፡ ካላበለጣችሁ ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ አትገቡም ፡ እላችኋለሁ ።

፩ሺ፮፻፭ ፱ ። ለቀደሙት ፡ ነፍስ ፡ አትግደል ፡ የተባለውን ፡ ሰምታችኋል ። ነፍስ ፡ ለገደለም ፡ ቅጣት፡ ይገባዋል ። እኔ ፡ ግን ፡ እላችኋለሁ ። በወንድሙ

እስመ ፡ ኵሉ ፡ ዘይትመዐዕ ፡ ላዕለ ፡ እኁሁ ፡ በከንቱ ፡ ደለወ ፡ ላዕሌሁ ፡ ኵነኔ ። ወዘይቤሎ ፡ ለእኁሁ ፡ ርሱሕ ፡ ዘፀርቅ ፡ ደለዎ ፡ ነውረ ፡ ማኅበር ። ወዘሂ ፡ ይቤሎ ፡ ለእኁሁ ፡ ዓብድ ፡ ደለዎ ፡ እሳተ ፡ ገሃነም ። ለእመ ፡ እንተ ፡ እምጻእከ ፡ መባእከ ፡ ነበ ፡ ምሥዋዕ ፡ ወተዘከርከ ፡ በሀየ ፡ ከመ ፡ ቦ ፡ እኁከ ፡ ዘተኀየሰከ ፡ ኅድግ ፡ ሀየ ፡ መባእከ ፡ ቅድመ ፡ ምሥዋዕ ፡ ወሑር ፡ ቅድመ ፡ ወተዐረቅ ፡ ምስለ ፡ እኁከ ፡ ወእምዝ ፡ ገቢእከ ፡ እብእ ፡ መባእከ ።

ላይ ፡ በከንቱ ፡ የሚቆጣ ፡ ሁሉ ፡ ቅጣት ፡ ይገባዋል ። ወንድሙንም ፡ ጨርቃም ፡ ወራዳ ፡ የሚለው ፡ የሸንጎ ፡ ቅጣት ፡ (ፍርድ) ፡ ይገባዋል ። ወንድሙንም ፡ ደንቆሮ ፡ የሚለው ፡ የገሃነም ፡ እሳት ፡ ተገባው ። መባዕህን ፡ ወደምሥዋዕ ፡ ብታመጣ ፡ ከዚያም ፡ የተጣላህ ፡ ወንድምህ ፡ እንዳለ ፡ ብታስብ ፡ መባዕህን ፡ ከዚያው ፡ ከምሥዋዑ ፡ ፊት ፡ ትተህ ፡ ሂድና ፡ አስቀድመህ ፡ ከወንድምህ ፡ ጋር ፡ ታረቅ ። ከዚህ ፡ በኋላም ፡ ተመልሰህ ፡ መባዕህን ፡ አግባ ።

፩፲፰፻፯ ሰማዕክሙ ፡ ዘተብህለ ፡ ለቀደምት ፡ ኢትዘምዉ ፡ ወአንሰ ፡ እብለክሙ ፡ ኵሉ ፡ ዘርእያ ፡ ለብእሲት ፡ ወፈተዋ ፡ ዘመወ ፡ ባቲ ፡ በልቡ ። ተብህለ ፡ ዘይድኅራ ፡ ለብእሲቱ ፡ የሀብ ፡ ላቲ ፡ መጽሐፈ ፡ ኅዳጋቲሃ ፡ ወአንሰ ፡ እብለክሙ ፡ ዘይድኅራ ፡ ለብእሲቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ነገረ ፡ ዝሙት ፡ ለሊሁ ፡ ረሰያ ፡ ዘማዊተ ፡ ወዘሂ ፡ አውሰበ ፡ ኅድግተ ፡ ናሁ ፡ ዘመወ ።

፩፲፰፻፯ ለቀደሙት ፡ አትሰስኑ ፡ የተባለውን ፡ ሰምታችኋል ። እኔ ፡ ግን ፡ እላችኋለሁ ። ሴትን ፡ አይቶ ፡ የወደዳት ፡ ሁሉ ፡ በልቡ ፡ አመነዘረባት ። ሚስቱን ፡ የሚፈታ ፡ ሰው ፡ የፍችዋን ፡ ደብዳቤ ፡ ይስጣት ፡ ተባለ ። እኔ ፡ ግን ፡ እላችኋለሁ ። ያለዝሙት ፡ ነገር ፡ ሚስቱን ፡ የሚፈታ ፡ ሰው ፡ ራሱ ፡ አመንዝራ ፡ አደረጋት ። የተፈታችዋንም ፡ ያገባ ፡ እነሆ ፡ አመነዘረ ።

፩፲፰፻፯ ወካዕበ ፡ ሰማዕክሙ ፡ ዘተብህለ ፡ ለቀደምት ፡ ኢትምሐል ፡ በሐሰት ፡ ወአግብእ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሐላከ ። ወአንሰ ፡ እብለክሙ ፡ ኢትምሐሉ ፡ ግሙራ ፡ ኢ ፡ በሰማይ ፡ እስመ ፡ መንበሩ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ወኢ ፡ በምድር ፡ እስመ ፡ መከየደ ፡ እገሪሁ ፡ ይእቲ ፡ ወኢ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ እስመ ፡ ይእቲ ፡ ሀገሩ ፡ ለንጉሥ ፡ ዐቢይ ። ወኢትምሐል ፡ በርእስከ ፡ እስመ ፡ ኢይትክሀለከ ፡ ትግበር ፡ እሐተ ፡ እምሥዕርተ ፡ ርእስከ ፡ ኢጸዓዳ ፡ ወኢጸሊመ ፡ እላ ፡ ይኩን ፡ ቃልክሙ ፡ እመኒ ፡ እወ ፡ እወ ፡ ወእመኒ ፡ አልቦ ፡ አልቦ ፡ ወዘፈድፈደ ፡ እምዝንቱ ፡ እምእኩይ ፡ ውእቱ ።

፩፲፰፻፯ ዳግመኛም ፡ ለቀደሙት ፡ የተባለውን ፡ ሰምታችኋል ። በሐሰት ፡ አትማል ። መሐላህንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መልስ ። እኔ ፡ ግን ፡ እላችኋለሁ ። ከቶ ፡ አትማሉ ። በሰማይም ፡ ቢሆን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዙፋን ፡ ነውና ። በምድርም ፡ ቢሆን ፡ የእግሩ ፡ መረገጫ ፡ ናትና ። በኢየሩሳሌምም ፡ ቢሆን ፡ የታላቁ ፡ ንጉሥ ፡ አገር ፡ ናትና ። በራስህም ፡ አትማል ። ከራስህ ፡ ጠጉር ፡ አንዲቱን ፡ ነጭ ፡ ወይም ፡ ጥቁር ፡ ልታደርግ ፡ አትችልምና ። ነገራችሁ ፡ አዎን ፡ አዎን ፡ ወይም ፡ አይደለም ፡ አይደለም ፡ ይሁን ፡ እንጂ ። ከዚህም ፡ የበዛው ፡ (የወጣ) ፡ ከክፉ ፡ ወገን ፡ ነው ።

፩፲፰፻፰ ሰማዕክሙ ፡ ዘተብህለ ፡ ዓይን ፡ ቤዛ ፡ ዓይን ፡ ወሰን ፡ ቤዛ ፡ ስን ፡ ወአንሰ ፡ እብለክሙ ፡ ኢትትቃወምዎ ፡ ለእኩይ ፡ በእኩይ ፡ ግሙራ ። ወለዘሂ ፡ ጸፍዐከ ፡ መልታሕቴከ ፡ ዘየማን ፡ ሚጥ ፡ ሎቱ ፡ ካልእታሂ ። ወለዘሂ ፡ ፈቀደ ፡ ይትዓገልከ ልብሰከ ፡ ኅድግ ፡ ሎቱ ፡ ክዳነከሂ ። ወለዘሂ ፡ ዐበጠከ ፡ ፩ደ ፡ ምዕራፈ ፡ ሑር ፡ ምስሌሁ ፡ ፪ተ ፡ ምዕራፈ ። ምዕራፍ ፡ ብሂል ፡ ብጽሐተ ፡ እንሥእ ንጻሬ ፡ ወለዘሰአለከ ፡ ሀበ ፡ ወለዘፈቀደ ፡ ይትለቃሕ ፡ እምኔከ ፡ ኢትክልእ ። ሰማዕክሙ ፡ ዘተብህለ ፡ አፍቅር ፡ ቢጸከ ፡ ወጽላእ ፡ ጸላኢከ ። ወአንሰ ፡ እብለክሙ ፡ አፍቅሩ ፡ ጸላእተክሙ ፡

፩፲፰፻፰ ለቀደሙት ፡ የተባለውን ፡ ሰምታችኋል ። ዓይን ፡ የዓይን ፡ ቤዛ ፡ ነው ። ጥርስም ፡ የጥርስ ፡ ቤዛ ፡ ነው ። እኔ ፡ ግን ፡ እላችኋለሁ ። ክፉውን ፡ በክፉ ፡ ከቶ ፡ አትቃወሙት ። ቀኝ ፡ ፊትህን ፡ በጥፊ ፡ ለመታህ ፡ ሁለተኛዋንም ፡ መልስለት ። እጀጠባብህን ፡ ሊቀማህ ፡ ለወደደም ፡ መጐናጸፊያህን ፡ ተውለት ። አንድ ፡ ምዕራፍ ፡ ቢመልስልህ ፡ (ቢወስድህ) ፡ ሁለት ፡ ምዕራፍ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ሂድ ። ምዕራፍ ፡ ማለት ፡ ማየትን ፡ ማንሣት ፡ የሚደርስበት ፡ ነው ። (የዓይን ፡ እሰተ ያየት ፡ የሚደርስበት ፡ ነው) ፡ ለለመነህም ፡ ስጠው ። ከአንተ ፡ ሊበደር ፡ የሚሻውን ፡ አት

ወደኀርዎሙ ፡ ለእለ ፡ ይረግሙክሙ ፡ ወእሠ
ንዩ ፡ ለእለ ፡ ይጸልኡክሙ ፡ ወጸልዩ ፡ ዲበ ፡ እለ
ይትዔገሉክሙ ፡ ወይሰድዱክሙ ፡ ወያቴክዙ
ክሙ ፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ ውሉዶ ለእቡክሙ ፡ ዘበ
ሰማያት ፡፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ያሠርቅ ፡ ፀሐየ ፡
ላዕለ ፡ ኄራን ፡ ወእኩያን ፡ ወያዘንም ፡ ዝናመ ፡
ላዕለ ፡ ጻድቃን ፡ ወዐማፅያን ፡ ኩኑ ፡ እንት
ሙ፡ ፡ ፍጹማነ ፡ ከመ ፡ እቡክሙ ፡ ሰማያዊ ፡
ፍጹም ፡ ውእቱ ፡፡

፩ሺ፮፻፱ ርእዩ ፡ ኢትግበሩ ፡ ጽድቀክሙ ፡ በቅድመ ፡
ሰብእ ፡ ከመ ፡ ይርአዩክሙ ፡ እመ ፡ አኮሰ ፡
ዓስብ ፡ አልብክሙ ፡ በኀበ ፡ እቡክሙ ፡ በሰማ
ያት ፡፡ ወሶበሂ ፡ ትጼልዩ ፡ ኢትኩኑ ፡ ከመ ፡ መደ
ልዋን ፡ እማን ፡ እብለክሙ ፡ ከመ ፡ እሙንቱ ፡
ነሥኡ ፡ ዕሤቶሙ ፡ ወሠለጡ ፡ ዓሰቦሙ ፡፡ ወሶ
በሂ ፡ ትጸውሙ ፡ ኢትቍጽሩ ፡ ገጽክሙ ፡ ከመ ፡
መደልዋን ፡፡

፩ሺ፮፻፲ ኢትዘግቡ ፡ ለክሙ ፡ መዝገበ ፡ በውስተ ፡
ምድር ፡ ዳእሙ ፡ በውስተ ፡ ሰማያት ፡ ውኀበ ፡
ሀሎ ፡ መዝገብክሙ ፡ ህየ ፡ ይሄሉ ፡ ልብክሙ ፡፡
ኢይክል ፡ ፩ዱ ፡ ገብር ፡ ተቀንዮ ፡ ለ፪ቱ ፡ አጋእ
ዝት ፡ ኢትክሉኑ ፡ ተቀንዮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ወለንዋይ ፡፡ ኅሡ ፡ ቅድመ ፡ መንግሥተ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ወጽድቆ ፡ ወዝንቱሰ ፡ ኵሉ ፡ ይትዌ
ሰከክሙ ፡፡ ኢተሐልዩ ፡ ለጌሠም ፡ እስመ ፡ ጌሠ
ምሰ ፡ ትሔሊ ፡ ለርእሳ ፡ ወየአክላ ፡ ለዕለት ፡
እኪያ ፡፡

፩ሺ፮፻፲፩ ኢትኰንኑ ፡ ከመ ፡ ኢትትኰነኑ ፡ ቅድመ ፡
አውፅእ ፡ ሠርዌ ፡ እምዓይንከ ፡ ወይእተ ፡ ጊዜ ፡
ትሬእር ፡ ከመ ፡ ታውፅእ ፡ ሐሠረ ፡ ዘውስተ ፡
ዓይነ ፡ ቢጽከ ፡፡ ኢተሀቡ ፡ ቅድሳተ ፡ ለከለባት ፡
ሰእሉ ፡ ወይትወሀበክሙ ፡ ኅሡ ፡ ወትረክቡ ፡
ጐድጕዱ ፡ ወይትረኀው ፡ ለክሙ ፡፡ በከመ ፡
ትፈቅዱ ፡ ይግበሩ ፡ ለክሙ ፡ ሰብእ ፡ ግበሩ ፡
ሎሙ ፡ እንትሙሂ ፡ እስመ ፡ ከመዝ ፡ ውእቱ ፡
ኦሪትሂ ፡ ወነቢያትሂ ፡፡ ባኡ ፡ እንተ ፡ ጸባብ ፡
አንቀጽ ፡ እንተ ፡ ትወስድ ፡ ውስተ ፡ ሕይወት ፡
እስመ ፡ ሰፊሕት ፡ ይእቲ ፡ ለሐዊር ፡ ወፍኖትሰ ፡
ርኅብት ፡ ይእቲ ፡ እንተ ፡ ትወስድ ፡ ውስተ ፡
ኀጕል ፡፡ ተዓቀቡ ፡ እንከ ፡ እምሐሳውያን ፡ ነቢ
ያት ፡ እለ ፡ ይመጽኡ ፡ ኀቤክሙ ፡ በአልባሰ ፡



ክልክለው ፡፡ ጓደኛህን ፡ ውደድ ፡ ጠላትህንም ፡
ጥላ ፡ የተባለውን ፡ ሰምታችኋል ፡፡ እኔ ፡ ግን ፡
እላችኋለሁ ፡፡ ጠላታችሁን ፡ ውደዱ ፡፡ የሚረግ
ሙአችሁንም ፡ መርቋቸው ፡፡ ለሚጠሉአችሁም
መልካም ፡ አድርጉ ፡፡ ለሚቀሙአችሁና ፡ ለሚ
ያባርሯችሁ ፡ ለሚያሳዝኑአችሁም ፡ ጸልዩ ፡፡
ለሰማያት ፡ አባታችሁ ፡ ልጆቹ ፡ ትሆኑ ፡ ዘንድ፡
እርሱ ፡ ለደጎችና ፡ ለክፉዎች ፡ ፀሐይን ፡ ያወጣ
ልና ፡፡ ዝናምንም ፡ ለጻድቃንና ፡ ለዓመፀኞች ፡
ያዘንማልና ፡፡ ሰማያዊ ፡ አባታችሁ ፡ ፍጹም ፡
እንደሆነ እናንተም ፡ ፍጹማን ፡ ሁኑ ፡፡

፩ሺ፮፻፱ ያዩላችሁ ፡ ዘንድ ፡ ጽድቃችሁን ፡ በሰዎች ፡
ፊት ፡ እንዳታደርጉ ፡ እዩ ፡፡ ያለዚያስ ፡ በሰማ
ያት ፡ ዋጋ ፡ የላችሁም ፡ በምትጸልዩበትም ፡ ጊዜ ፡
እንደ ፡ ግብዞች ፡ አትሁኑ ፡፡ እነርሱ ፡ ዋጋቸውን
እንደ ፡ ወሰዱ ፡ ዋጋቸውንም ፡ እንደጨረሱ ፡
እውነት ፡ እላችኋለሁ ፡፡ በምትጾሙም ፡ ጊዜ ፡
እንደ ፡ ግብዞች ፡ ፊታችሁን ፡ አትቋጥሩ ፡፡

፩ሺ፮፻፲ በሰማያት ፡ እንጂ ፡ በምድር ፡ ለእናንተ ፡ ድል
ብን ፡ አታድልቡ ፡፡ ድልባችሁ ፡ ካለበት ፡ ዘንድ
ከዚያ ፡ ልባችሁ ፡ ይኖራል ፡፡ አንድ ፡ ባሪያ ፡ ለሁ
ለት ፡ ጌቶች ፡ መገዛት ፡ አይችልም ፡፡ ለእግዚአ
ብሔርና ለገንዘብ ፡ መገዛት ፡ አትችሉም ፡፡ አስ
ቀድማችሁ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥትና ፡
ጽድቁን ፡ ሹ ፡፡ (ፈልጉ) ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ ይጨ
መርላችኋል ፡፡ ለነገ ፡ አታስቡ ፡፡ ነገ ፡ ለራሱዋ ፡
ታስባለችና ፡ ለዕለትም ፡ ክፋቷ ፡ ይበቃታል ፡፡

፩ሺ፮፻፲፩ እንዳይፈረድባችሁ ፡ አትፍረዱ ፡፡ አስቀድ
መህ ፡ ከዓይንህ ፡ ጉድፍን ፡ አውጣ ፡፡ ያን ፡
ጊዜ ፡ በባልንጀራህ ፡ ዓይን ፡ ያለውን ፡ ጉድፍ ፡
ለማውጣት ፡ ታያለህ ፡፡ የተቀደሰውን ፡ ለው
ሾች ፡ አትስጡ ፡፡ ለምኑ ፡ ይሰጣችኋልም ፡፡ ሹ ፡
(ፈልጉ) ፡ ታገኙማላችሁ ፡፡ ደጅ ፡ ምቱ ፡ ይከፈትላ
ችኋልም ፡፡ ሰዎች ፡ ሊያደርጉላችሁ ፡ እንደምት
ወዱ ፡ እናንተም ፡ አድርጉላቸው ፡፡ ኦሪትም ፡
ነቢያትም ፡ እንደዚሁ ፡ ነውና ፡፡ ወደ ፡ ሕይ
ወት ፡ በምትወስደው ፡ በጠባብ ፡ በር ፡ ግቡ ፡፡
ለመሄድ ፡ ሰፊ ፡ ናትና ፡፡ ወደጥፋት ፡ የምትወሰ
ደው ፡ መንገድ ፡ ግን ፡ ሰፊ ፡ ናት ፡፡ የበግ ፡ ልብ
ስን ፡ ለብሰው ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ከሚመጡ ፡ ከሐ
ሰተኞች ፡ ነቢያት ፡ ተጠበቁ ፡፡ በውስጣቸው ፡

አባግዕ ፡ ወእንተ ፡ ውስጦሙሰ ፡ ተኵላት ፡
መሠጥ ፡ ወእምፍሬሆሙ ፡ አእምርዎሙ ።
፩ሺ፮፻፲፪ እኮ ፡ ኵሉ ፡ ዘይብለኒ ፡ እግዚኦ ፡ እግዚኦ ፡ ዘይ
በውእ ፡ ውስተ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ አላ ፡
ዘይገብር ፡ ፈቃዶ ፡ ለአቡየ ፡ ዘበሰማያት ። እብ
ለክሙ ፡ ከመ ፡ ኵሉ ፡ ቃል ፡ ዘይነብብ ፡ ቦቱ ፡
ሰብእ ፡ ዕሩዐ ፡ ያገብእዎ ፡ ቃለ ፡ ተሠጥዎ ፡ በእን
ቲአሁ ፡ በዕለተ ፡ ደይን ። ወኵሉ ፡ ዘይገብር ፡
ሥምረቶ ፡ ለአቡየ ፡ ዘበሰማያት ፡ ውእቱ ፡ እኁ
የኒ ፡ ወእኅትየኒ ፡ ወእምየኒ ። ኢይብለከ ፡ እስከ ፡
፯ቱ ፡ ጊዜያት ፡ ሥረዮ ፡ ለእኁከ ፡ አላ ፡ ሰብዓ ፡
ጊዜያተ ፡ በበስብዕ ። ዘይፈቅድ ፡ ይኩን ፡ ዐቢየ ፡
በውስቴትክሙ ፡ ይኩን ፡ ላእከ ፡ ወዘይፈቅድ ፡
እምኔክሙ ፡ ይኩን ፡ ሊቀ ፡ ይኩንክሙ ፡ ገብረ ።
አማን ፡ እብለክሙ ፡ እመ ፡ ኢተመየጥክሙ ፡
ወኢኮንክሙ ፡ ከመዝ ፡ ሕፃን ፡ ኢትበውእዋ ፡
ለመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ወዘሂ ፡ ተትሕተ ፡
ከመ ፡ ዝንቱ ፡ ሕፃን ፡ ዐቢይ ፡ ውእቱ ፡ በመንግ
ሥተ ፡ ሰማያት ፡ አማን ፡ እብለክሙ ፡ ለእመ ፡
ብክሙ ፡ ሃይማኖት ፡ ወኢናፈቅሙ ፡ ሶበ ፡ ትቤ
ልዎ ፡ ለዝንቱ ፡ ደብር ፡ ፍልስ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡
ይከውን ፡ በከመ ፡ ነበብክሙ ። ወለኵሉ ፡ ዘትስ
እልዎ ፡ በጸሎት ፡ ወበሃይማኖት ፡ ትረክብዎ ።"

፩ሺ፮፻፲፫ ማርቆስ ፡ ዘ፲ወ፱ቱ ፡ "ወእሉ ፡ እሙንቱ ፡ እለ
ውስተ ፡ ሦክ ፡ ተዘርኡ ፡ እሙንቱ ፡ እለ ፡ ይሰ
ምዑ ፡ ቃለ ፡ ወይመውዖሙ ፡ ጻሕቀ ፡ ዝንቱ ፡
ዓለም ፡ ወብዕል ፡ ሰፋጢት ፡ ወኵሉ ፡ ፍትወ
ታት ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ የሐውሩ ፡ ወየሐንቅዎ ፡
ለቃል ፡ ወኢይፈሪ ፡ በላዕሌሆሙ ። አልቦ ፡
ኅቡእ ፡ ዘኢይትከሠት ፡ ወአልቦ ፡ ክቡት ፡ ዘኢ
ያስተርኢ ።"
፩ሺ፮፻፲፬ ሉቃስ ፡ ዘ፲ወ፫ቱ ፡ "አሌ ፡ ለክሙ ፡ አብዕልት
እስመ ፡ ሠለጥክሙ ፡ ዓስበክሙ ። አሌ ፡ ለክሙ
እለ ፡ ትጸግቡ ፡ ይእዜ ፡ እስመ ፡ አንትሙ ፡ ትር
ኀቡ ። አሌ ፡ ለክሙ ፡ እለ ፡ ትስሕቁ ፡ ይእዜ ፡
እስመ ፡ አንትሙ ፡ ትበክዩ ፡ ወተኀዝኑ ። አሌ ፡
ለክሙ ፡ ሶበ ፡ ይብሉ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ቃለ ፡
ሠናየ ፡ ላዕሌክሙ ፡ እስመ ፡ ከማሁ ፡ ረሰይዎሙ
ለአበዊክሙ ፡ ነቢያት ፡ ሐሳውያን ።
፩ሺ፮፻፲፭ ዘ፴ወ፫ቱ ፡ ኢትትፌሥሑ ፡ በዝ ፡ እስመ ፡ አጋ
ንንት ፡ ይገንዩ ፡ ለክሙ ፡ ተፈሥሑሰ ፡ እስመ ፡



ግን ፡ ነጣቂዎች ፡ ተኵላዎች ፡ ናቸው ። ከፍሬያ
ቸውም ፡ የተነሣ ፡ ዕወቋቸው ።
፩ሺ፮፻፲፪ አቤቱ ፡ አቤቱ ፡ የሚለኝ ፡ ሁሉ ፡ ወደ መንግ
ሥተ ፡ ሰማያት ፡ የሚገባ ፡ አይደለም ። በሰማ
ያት ፡ ያለ ፡ የአባቴን ፡ ፈቃድ ፡ የሚፈጽም ፡
ነው ፡ እንጂ ። (ማቴ ፡ ፯ - ፳) ። ሰው ፡ በዋዘኛ
ነት ፡ በሚናገረው ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡
ስለእርሱ ፡ የመልስ ፡ ቃል ፡ እንዲመልስለት ፡
እነግራችኋለሁ ። በሰማያት ፡ ያለ ፡ የአባቴን ፡
ፈቃድ ፡ የሚያደርግ ፡ ሁሉ ፡ ወንድሜ ፡ እኅ
ቴም ፡ እናቴም ፡ እርሱ ፡ ነው ። (ማቴ ፡ ፲፪ ፡
፵፯ ። ፵፱ - ፶) ። ለወንድምህ ፡ እስከ ፡ ፯ ፡ ጊዜ ፡
ይቅር ፡ በል ፡ አልልህም ። በየሰባቱ ፡ ፸ ፡ ጊዜ ፡
ነው ፡ እንጂ ። (ማቴ ፡ ፲፰ ፡ ፳፩ - ፳፪) ። በእናን
ተ ፡ ውስጥ ፡ ታላቅ ፡ ሊሆን ፡ የሚወድ ፡ አገል
ጋይ ፡ ይሁን ። ከእናንተም ፡ አለቃ ፡ ሊሆን ፡
የሚወድ ፡ ባሪያ ፡ ይሁናችሁ ። እውነት ፡ እላች
ኋለሁ ፡ ተመልሳችሁ ፡ እንደዚህ ፡ ሕፃን ፡ ካል
ሆናችሁ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ አትገቡአ
ትም ። (ማር ፡ ፱ ፡ ፴፫ - ፴፯) ። እውነት ፡ እላች
ኋለሁ ። ሃይማኖት ፡ ካላችሁ ፡ ካልተጠራጠራ
ችሁም ፡ ይህን ፡ ተራራ ፡ ወደ ባሕር ፡ ፍለስ ፡
ብትሉት ፡ እንደተናገራችሁ ፡ ይሆናል ። በጸሎ
ትና ፡ በሃይማኖት ፡ የምትለምኑትን ፡ ሁሉ ፡
ታገኙታላችሁ ። (ማቴ ፡ ፳፩ ፡ ፳፩ - ፳፪) ።
፩ሺ፮፻፲፫ ማርቆስ ፡ ፲፱ ። በእሾህ ፡ ውስጥ ፡ የተዘሩ ፡
እሊህ ፡ ናቸው ። ትምህርትን ፡ ሰምተው ፡
የዚህ ፡ ዓለም ፡ አሳብ ፡ አታላዩት ፡ ብዕልም ፡
የሚኖሩባት ፡ ምኞትም ፡ (ፍትወትም) ፡ ሁሉ ፡
ድል ፡ የሚነሣቸው ፡ ናቸው ። ትምህርቱንም ፡
ያንቁታል ። በላያቸውም ፡ አያፈራም ። (ማር ፡
፬ ፡ ፲፰ - ፳) ። የማይገለጽ ፡ ስውር ፡ የለም ። የማ
ይታይም ፡ ሽሽግ ፡ የለም ። (ሉቃ ፡ ፲፪ ፡ ፪ )።
፩ሺ፮፻፲፬ ሉቃስ ፡ ፲፫ ። ባለጸጎች ፡ ወዮላችሁ ። ዋጋች
ሁን ፡ ጨርሳችኋልና ። ዛሬ ፡ የምትጠግቡ ፡
ወዮላችሁ ። እናንተ ፡ ትራባላችሁና ። ዛሬ ፡
የምትስቁ ፡ ወዮላችሁ ። እናንተ ፡ ታለቅሳላች
ሁና ። ታዝኑማላችሁ ። ሰዎች ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡
መልካም ፡ ነገር ፡ ባወሩ ፡ ጊዜ ፡ ወዮላችሁ ።
ሐሰተኞች ፡ ነቢያት ፡ አባቶቻችሁን ፡ እንደዚሁ
አደርገዋቸዋልና ። (ሉቃ ፡ ፮ ፡ ፳፬ - ፳፮) ።
፩ሺ፮፻፲፭ ፴፫ ። በዚህ ፡ ደስ ፡ አይበላችሁ ። አጋንንት ፡
ይገዙላችኋልና ። ነገር ፡ ግን ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ·

ተጽሕፈ ፡ አስማቲክሙ ፡ በሰማያት ።

፩ሺ፯፻፲፮ ዘሃወፀ፬ቱ ፡ ወሶበ ፡ ይጼውዑከ ፡ ውስተ ፡ ምሳሕ ፡ ሐር ፡ ወርፍቅ ፡ ውስተ ፡ ዘይቴሐት ፡ ምርፋቅ ፡ እስመ ፡ ሆሉ ፡ ዘአልዐለ ፡ ርእሶ ፡ የኅሥር ፡ ወዘአትሐተ ፡ ርእሶ ፡ ይከብር ። ወሶበ ፡ ትገብር ፡ በዓለ ፡ አው ፡ ምሳሐ ፡ ኢትጸውዕ ፡ አዕርክቲከ ፡ ወአኃዊከ ፡ ወማኅፈረከ ፡ ወአዝማዲከ ፡ ወአግዋረከ ፡ አብዕልተ ፡ ከመ ፡ ለእመ ፡ ቦ ፡ ሶበ ፡ ይጼውዑከ ፡ እሙንቱኒ ፡ ካዕበ ፡ ይከውንከ ፡ ፍዳ ፡ በኀቤሆሙ ። ወባሕቱ ፡ ሶበ ፡ ትገብር ፡ በዓለከ ፡ ጸውዕ ፡ ነዳያነ ፡ ወጽኑሳነ ፡ ወመፃጕዓነ ፡ ወዕዉራነ ፡ ወብፁዕ ፡ አንተ ፡ እስመ ፡ አልቦሙ ፡ ዘይፈድዩከ ፡ ወትትዐሠይ ፡ ባሕቱ ፡ አመ ፡ ትንሣኤ ፡ ጻድቃን ።”

፩ሺ፯፻፲፯ ዮሐንስ ፡ ዘ፫ቱ ፡ ዘኢተወልደ ፡ አማይ ፡ ወእመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኢይክል ፡ በዊእ ፡ ውስተ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ። ወአንትሙሰ ፡ ትብሉኒ ፡ ሊቅነ ፡ ወእግዚእነ ፡ ወሠናየ ፡ ትቤሉ ፡ አስመ ፡ ከማሁ ፡ አነ ፡ ሊቅክሙ ፡ ወእግዚእክሙ ፡ ወእመሰ ፡ አነ ፡ ሊቅከሙ ፡ ወእግዚእከሙ ፡ ነዋ ፡ ሐፀብኩ ፡ እገሪከሙ ፡ ወከማሁ ፡ አንትሙኒ ፡ ይደልወክሙ ፡ ትሕፅቡ ፡ እግረ ፡ ቢጽከሙ ፡ እስመ ፡ አርአያየ ፡ ወሀብኩክሙ ።” ዘሮሜ ፡ ፲ ወ፫ቱ ፡ “ብፁዕ ፡ ብእሲ ፡ ዘኰነና ፡ ለነፍሱ ፡ በዘተውህቦ ፡ አእምሮ ።”

፩ሺ፯፻፲፰ ዘቆሮንቶስ ፡ ፫ቱ ፡ ወለእመቦ ፡ ዘይሰመይ ፡ እምኔክሙ ፡ እኅወ ፡ ወኮነ ፡ ዘማዌ ፡ አው ፡ ተዓጋሌ ፡ እው ፡ መምለኬ ፡ ጣዖት ፡ እው ፡ ጸአሌ ፡ አው ፡ ስካሬ ፡ አው ፡ ሀያዶ ፡ ኢትትሐወልዎ ፡ በመብልዕ ።

፩ሺ፯፻፲፱ ዘ፮ቱ ፡ ወለምንትኑ ፡ ኢትትገፍዑ ፡ ወለምንትኑ ፡ ኢትትሀየዱ ፡ ወባሕቱ ፡ አንትሙ ፡ ትገፍዑ ፡ ወተሀይዱ ፡ ካዕበ ፡ አኃዊክሙ ፡ ኢተአምሩኑ ፡ ከመ ፡ ሀማዕያን ፡ ኢይወርስዋ ፡ ለመንግሥተ ፡ እግዚአብሔር ። ኢያስሕትክሙ ፡ ኢዘማውያን ፡ ወኢ ፡ እለ ፡ ያመልኩ ፡ ጣዖተ ፡ ወኢ ፡ እለ ፡ የሐውርዎሙ ፡ ወኢ ፡ አለ ፡ የሐውሩ ፡ ተባዕተ ፡ ወኢ ፡ ተዓጋልያን ፡ ወኢ ፡ ሰረ



ስማችሁ ፡ በሰማይ ፡ ተጽፏልና ። (ሉቃ ፡ ፲ ፡ ፳) ።

፩ሺ፯፻፲፮ ፶፬ ። ወይምሳ ፡ በጠሩህም ፡ ጊዜ ፡ ሂደህ ፡ ከዝቅተኛ ፡ መቀመጫ ፡ ተቀመጥ ። ራሱን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደረገ ፡ ሁሉ ፡ ይዋረዳልና ። ራሱንም ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ ያደረገ ፡ ይከብራልና ። በዐል ፡ ወይም ፡ ግብዣ ፡ በአደረግህ ፡ ጊዜ ፡ ወዳጆችህንና ፡ ወንድሞችህን ፡ እማቾችህንም ፡ ዘመዶችህንና ፡ ጎረቤቶችህን ፡ ባለጸጎችንም ፡ አትጥራ ። ምናልባት ፡ እነርሱም ፡ በጠሩህ ፡ ጊዜ ፡ በእነርሱም ፡ ዘንድ ፡ ደግሞ ፡ ብድራት ፡ ይሆንሃል ። ነገር ፡ ግን ፡ በዓል ፡ በምታደርግበት ፡ ጊዜ ፡ ድኆችንና ፡ ችግረኞችን ፡ ጎባጦችን ፡ ዕውሮችንም ፡ ጥራ ። ብፁዕም ፡ ትሆናለህ ። የሚከፍሉት ፡ የላቸውምና ። በጻድቃን ፡ ትንሣኤ ፡ ጊዜ ፡ ዋጋህን ፡ ታገኛለህ ፡ እንጂ ። (ሉቃ ፲፬ ፡ ፲፪ - ፲፭) ።

፩ሺ፯፻፲፯ ዮሐንስ ፡ ፫ ። ከውሀና ፡ ከመንፈስ ፡ ያልተወለደ ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ መግባት ፡ አይችልም ። (ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፭ )። እናንተስ ፡ አለቃችንና ፡ ጌታችን ፡ ትሉኛላችሁ ። መልካምም ፡ ትላላችሁ ። እንደዚሁ ፡ እኔ ፡ አለቃችሁና ፡ ጌታችሁ ፡ ነኝና ። እነሆ ፡ እግራችሁን ፡ አጠብሁ ። እንደዚሁም ፡ እናንተ ፡ የባልንጀራችሁን ፡ እግር ፡ ልታጥቡ ፡ ይገባችኋል ። ምሳሌዬን ፡ ሰጥቻችኋለሁና ። (ዮሐ ፡ ፲፫ ፡ ፲፫ - ፲፮) ። ሮሜ ፡ ፲፫ ። በተሰጠው ፡ አእምሮ ፡ ሰውነቱን ፡ የቀጣት ፡ ሰው ፡ ብፁዕ ፡ ነው ። (ሮሜ ፡ ፲፬ ፡ ፳፪) ።

፩ሺ፯፻፲፰ ቆሮንቶስ ፡ ፭ ። ከእናንተ ፡ ወገን ፡ ወንድም ፡ የሚባል ፡ ቢኖር ፡ ዘማዊ ፡ ወይም ፡ ቀማኛ ፡ ወይም ፡ ጣዖት ፡ የሚያመልክ ፡ ወይም ፡ ተሳዳቢ ፡ ወይም ፡ ሰካራም ፡ ወይም ፡ ነጣቂ ፡ ቢሆን ፡ በመብል ፡ ጊዜ ፡ አትቀላቀሉት ። (፩ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፲፩ - ፲፪) ።

፩ሺ፯፻፲፱ ፮ ። ለምን ፡ አትገፉም ? ለምንስ ፡ አትቀሙም ? ነገር ፡ ግን ፡ እናንተ ፡ ትገፋላችሁ ። (ትበድላላችሁ) ፡ ዳግመኛም ፡ ወንድሞቻችሁን ፡ ትቀማላችሁ ። ዓመፀኞች ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ እንደማይወርሱአት ፡ አታውቁምን ? ዘማውያን ፡ ቢሆኑ ፡ ጣዖት ፡ የሚያመልኩም ፡ የሚሄዱባቸውም ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ወንድ የሚሄዱ ፡ ወይም ፡ ቀማኞች ፡ ወይም ፡ ሌቦች ፡

ቅት ፡ ወኢ ፡ ስካርያን ፡ ወኢ ፡ ጸአልያን ፡ ወኢ ሀያድያን ፡ እሉ ፡ ኵሎሙ ፡ ኢይወርስዋ ፡ ለመን ግሥተ ፡ እግዚአብሔር ።

፩ሺ፯፻፳ ዘ፲ወ፯ቱ ፡ ቅንኢ ፡ ለእንተ ፡ ተዐቢ ፡ ጸጋ ፡ አንስ ፡ አርእየክሙ ፡ ካዕበ ፡ ፍኖተ ፡ ካልአ ፡ ዘይኄይስ ፡ ፈድፋደ ። ወእመኒ ፡ ነበብኩ ፡ በልሳነ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ ወነገረ ፡ መላእክት ፡ ወእመኒ ፡ ተነበይኩ ፡ ወአእመርኩ ፡ ኵሎ ፡ ዘኅቡእ ፡ ወኵሎ ፡ ዘጥበብ ፡ ወእመኒ ፡ ብየ ፡ ሃይማኖት ፡ እስከ ፡ አፈልስ ፡ አድባረ ፡ ወእመኒ ፡ አብላዕኩ ፡ ለነዳያን ፡ ኵሎ ፡ ዘብየ ፡ ወዓዲ ፡ ሥጋየኒ ፡ ለውዕየተ ፡ እሳት ፡ ወተፋቅሮ ፡ አል ብየ ፡ አልቦ ፡ ዘረባኅኩ ። እስመ ፡ ዘቦቱ ፡ ተፋ ቅሮ ፡ ርኁሩኅ ፡ ወተዓጋሢ ፡ ውእቱ ፡ ሠናየ ፡ ተላጽቆ ፡ ኢይቀንእ ፡ ወኢይትሀወክ ፡ ኢይትዔ በይ ፡ ወኢያመጽእ ፡ ዘያስተኀፍር ፡ ወኢየኀ ሥሥ ፡ ተድላ ፡ ለባሕቲቱ ፡ ኢይትመዐዕ ፡ ወኢይሔሊ ፡ እኩየ ፡ ኢይትፌሣሕ ፡ በግፍዕ ፡ ወይትፌሣሕ ፡ በጽድቅ ፡ ይትዔገሥ ፡ በኵሉ ፡ ወበኵሉ ፡ ወየአምን ። ወይትዌከል ፡ በኵሉ ፡ ወይፀመድ ፡ በኵሉ ፡ ወእሉ ፡ እሙንቱ ፡ ፫ቱ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ሃይማኖት ፡ ወተስፋ ፡ ወተፋ ቅሮ ፡ ወእምነ ፡ ኵሎሙ ፡ የዓቢ ፡ ተፋቅሮ ።

፩ሺ፯፻፳፩ ዘ፲ወ፰ቱ ፡ ወባሕቱ ፡ ኩኑ ፡ ከመ ፡ ሕፃናት ፡ ለገቢረ ፡ እኩይ ፡ ወፍጹማነ ፡ በምክርክሙ ።

፩ሺ፯፻፳፪ ዘቆሮንቶስ ፡ ፫ቱ ፡ እስመ ፡ ሀለወነ ፡ ለኵልነ ፡ ከመ ፡ ንቁም ፡ ቅድመ ፡ መንበሩ ፡ ለክርስቶስ ፡ ወይፈድዮ ፡ ለለ፩ዱ ፡ እምኔነ ፡ በከመ ፡ ምግ ባሩ ፡ ዘገብረ ፡ በሥጋሁ ፡ እመኒ ፡ ሠናየ ፡ ወእ መኒ ፡ እኩየ ።

፩ሺ፯፻፳፫ ዘ፬ቱ ፡ ዑቁ ፡ ኢትረስዩ ፡ ምክንያተ ፡ ዕቅፍት ፡ ለመኑሂ ፡ ከመ ፡ ኢይባእ ፡ ነውር ፡ ውስተ ፡ መልእክትነ ። ወባሕቱ ፡ ናግህድ ፡ ለሊነ ፡ በኵሉ ፡ ግብር ፡ ከመ ፡ ላእካነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንሕነ ፡ በዐቢይ ፡ ትዕግሥት ፡ ውስተ ፡ ፃዕር ፡ ወምንዳቤያት ፡ በሕማም ፡ ወበተቈስሎ ፡ በተ ሞቅሖ ፡ ወበስደት ፡ በጻማ ፡ ወበትጋህ ፡ በጾም ፡ ወበንጽሕና ፡ በአእምሮ ፡ ወበአንሞ ፡ መንፈስ ፡ በተፋቅሮ ፡ ወበተራኅርኆ ፡ በእንዚአ ፡ መን ፈስ ፡ ወበተፋቅሮ ፡ ዘእንበለ ፡ አድልዎ ፡ በነገረ ጽድቅ ፡ ወበኀይለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወበንዋየ ፡



ወይም ፡ ሰካራሞች ፡ ወይም ፡ ተሳዳቢዎች ፡ ወይም ፡ ነጣቂዎች ፡ አያስቷችሁ ። እሊህ ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ አይወር ሱአትም ። (፩ ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፯ - ፲፮) ።

፩ሺ፯፻፳ ፲፯ ። ለምትበልጠው ፡ ጸጋ ፡ ቅኑ ። እኔም ፡ ዳግ መኛ ፡ እጅግ ፡ የበለጠ ፡ ሌላ ፡ ጎዳና ፡ አሳያችኋ ለሁ ፡ በሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ቋንቋና ፡ በመላእክት ፡ ቋንቋ ፡ ብናገር ፡ ትንቢትም ፡ ብናገር ፡ የተሰወረ ውን ፡ ሁሉና ፡ የጥበብን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ባውቅ ፡ ተራራም ፡ እስከእፈልስ ፡ ድረስ ፡ ሃይማኖት ፡ ቢኖረኝ ፡ ያለኝንም ፡ ሁሉ ፡ ለድሆች ፡ ባበላ ፡ ዳግመኛም ፡ ሥጋዬን ፡ ለእሳት ፡ ቃጠሎ ፡ ብሰጥ ፡ ፍቅር ፡ ከሌለኝ ፡ የተጠቀምሁት ፡ የለም ። ፍቅር ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ርኅሩኅ ፡ ትዕግ ሥተኛም ፡ ነውና ። በፍቅር ፡ መልካም ፡ የሆነ ፡ (ፍጹም ፡ የሆነ) ፡ አይቀናም ። ቸልም ፡ አይልም አይታበይምም ። የሚያሳፍርም ፡ ነገር ፡ አያመ ጣም ። ለብቻውም ፡ ተድላን ፡ አይሻም ። አይበ ሳጭም ። ክፉም ፡ አያስብም ። በግፍዕ ፡ ደስ ፡ አይለውም ። በእውነት ፡ ግን ፡ ደስ ፡ ይለዋል ። በሁሉ ፡ ይታገሣል ። በሁሉም ፡ ይታመናል ። ጸንተውም ፡ የሚኖሩ ፡ ሃይማኖት ፡ ተስፋ ፡ ፍቅር ፡ ናቸው ። ከሁሉም ፡ ፍቅር ፡ ይበልጣል። (፩ ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፴፩ ። ፲፫ ፡ ፩ - ፲፫) ።

፩ሺ፯፻፳፩ ፲፰ ። ነገር ፡ ግን ፡ ክፉ ፡ ለመሥራት ፡ እንደ ፡ ሕፃናት ፡ ሁኑ ። በምክራችሁ ፡ ግን ፡ ፍጹማን ፡ ሁኑ ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፬ ፡ ፳) ።

፩ሺ፯፻፳፪ ቆሮንቶስ ፡ ፫ ። ሁላችንም ፡ በክርስቶስ ፡ ዙፋን ፡ ፊት ፡ እንቆም ፡ ዘንድ ፡ አለንና ። ከእ ኛም ፡ ለእየንዳንዱ ፡ መልካምም ፡ ቢሆን ፡ ክፉም ፡ ቢሆን ፡ በሥጋዉ ፡ እንደ ፡ ሠራው ፡ ሥራ ፡ ይከ ፍለዋል ። (፪ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፲) ።

፩ሺ፯፻፳፫ ፬ ። ለማንም ፡ የዕንቅፋት ፡ ምክንያት ፡ እንዳ ታደርጉ ፡ ዕወቁ ። በመልእክታችን ፡ ነውር ፡ እንዳይገባ ። ነገር ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገ ልጋዮች ፡ እንደመሆናችን ፡ ሥራን ፡ ሁሉ ፡ ራሳ ችን ፡ እንግለጥ ፡ እንጂ ። በጭንቅና ፡ በችግር ፡ ውስጥ ፡ በታላቅ ፡ ትዕግሥት ፡ በመታመም ፡ በመገረፍ ፡ በመታሰር ፡ በመሰደድ ፡ በድካም ፡ በትጋት ፡ በጾም ፡ በንጽሕና ፡ በዕውቀት ፡ መን ፈስን ፡ በማሰረዘም ፡ በፍቅር ፡ በመራራት ፡ ልቡናን ፡ ንጹሕ ፡ በማድረግ ፡ ያለማድላት ፡ በመፋቀር ፡ በእውነተኛ ፡ ነገር ፡ በእግዚአብ

ሐቅል ፡ ዘጽድቅ ፡ ዘእምየማን ፡ ወእምጸጋም ፡ በክብር ፡ ወበኀሣር ፡ በበረከት ፡ ወበመርገም ።”

፩ሺ፯፻፳፱ ዘገላትያ ፡ ወዑሩ ፡ በበይናቲክሙ ፡ ክበደ ፡ ቢጽክሙ ፡ ወኮሉ ፡ ብእሲ ፡ እምኔክሙ ፡ ያመክር ፡ ምግባሮ ፡ ወኢትስሐቱ ፡ እልቦ ፡ ዘያስተዓብዮ ፡ ለእግዚአብሔር ። ወዘዘርአ ፡ ሰብእ ፡ የአርር ፡ ወዘዘርአ ፡ ምግባራተ ፡ ሥጋ ፡ የዐርር ፡ እምውስቴቱ ፡ ሙስና ። ወዘይዘርእ ፡ ምግባራተ መንፈስ ፡ በመንፈስ ፡ የአርር ፡ ሕይወተ ፡ ዘለዓለም ። ወእምከመ ፡ ገበርነ ፡ ሠናየተ ፡ ኢንትሀከይ ፡ እስመ ፡ በለወነ ፡ በጊዜሁ ፡ ነአርር ፡ አምጣነ ፡ ብነ ፡ ዕለት ፡ ንግበር ፡ ሠናየ ፡ ለኵሉ ፡ ወኢንትሀከይ ፡ እንከ ።

፩ሺ፯፻፴ ዘኤፌሶን ፡ ፫ቱ ፡ አስተብቍዐክሙ ፡ ከመ ፡ ትሑሩ ፡ በበይደሉ ፡ ለጸዋዕክሙ ፡ እንተ ፡ ተጸዋዕክሙ ፡ እንዘ ፡ ታቴሕቱ ፡ ርእሰክሙ ፡ በኵሉ ፡ ጸሕቅ ፡ ወትዕግሥት ፡ ወየውሃት ። ወኩኑ ፡ እንዘ ፡ ትትዔገሡ ፡ በበይናቲክሙ ፡ በፍቅር ፡ ወትጸሕቁ ፡ ለዓቂበ ፡ ተስናእዎ ፡ በመንፈስ ፡ ወበማእሰረ ፡ ሰላም ፡ ከመ ፡ ትኩኑ ፡ ፩ደ ፡ ሥጋ ፡ ወ፩ደ ፡ መንፈስ ።

፩ሺ፯፻፴፩ ዘ፬ቱ ፡ ወዘእንበለ ፡ ይዕርብ ፡ ፀሐይ ፡ አቍርሩ ፡ መዓተክሙ ፡ ወኢተሀብዎ ፡ ፍኖተ ፡ ለሰይጣን ፡ ለአስሕቶትክሙ ። ዘይሰርቅኒ ፡ ኢይሰርቅ ፡ እንከ ፡ እላ ፡ ለይትገበር ፡ ወይጻሙ ፡ በእደዊሁ ፡ ለገቢረ ፡ ሠናይ ፡ በዘይረድኦ ፡ ለጽኑስ ። ወኵሉ ፡ ነገር ፡ ሕሡም ፡ ኢይፃእ ፡ እምአፉክሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ሠናይ ፡ በዘይትሐነጽ ፡ ትካዝክሙ ፡ ወኵሎ ፡ መሪረ ፡ ወቁጥዓ ፡ ወቍጥዓ ፡ ወከሳሐ ፡ ወዕርፈተ ፡ እኩየ ፡ እምላዕሌክሙ ፡ ምስለ ፡ ኵሉ ፡ እከይ ። ወኩኑ ፡ መሓርያነ ፡ ቢጽክሙ ፡ ወመሓሩ ፡ በከመ ፡ መሐረክሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ክርስቶስ ፡ ወተመሰሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ውሉድ ፡ ፍቁራን ። ወዝሙትሰ ፡ ወኵሉ ፡ ርኵስ ፡ ወበመዋ ፡ ኢይሰማዕ ፡ በላዕሌክሙ ፡ በከመ ፡ ኢይደልዎሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ነገረ ኀፍረት ፡ ወነገረ ፡ ዕበድ ፡ ወነገረ ፡ ስላቅ ፡ ወተላህዮ ፡ ለሣላ ፡ ክብር ፡ እንተ ፡ ኢትደሉ ፡ ኢትቅረብዋ ።

ዘፊልጵስዩስ ፡ ወፈጽሙ ፡ ከዊነ ፡ ፍሥሓየ ፡ ከመ ተሀልዉ ፡ በ፩ዱ ፡ ምክር ፡ ወበ፩ዱ ፡ ፍቅር ፡ ወአሐቲ ፡ ነፍስ ፡ ወኢትግበሩ ፡ በምንትኒ ፡ ተጋ



ሐር ፡ ኃይል ፡ ከቀኝና ፡ ከግራ ፡ በሚሆን ፡ በእውነት ፡ የጦር ፡ ዕቃ ፡ በክብር ፡ በመዋረድ ፡ በምርቃት ፡ በርግማንም ። (፪ ፡ ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፫ - ፲)።

፩ሺ፯፻፳፱ ገላትያ ። እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ የባልንጀራችሁን ፡ ሸክም ፡ ተሸከሙ ። ከእናንተ ፡ ወገን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሥራውን ፡ ይመርምር ። አትሳቱም ። እግዚአብሔርንም ፡ የሚያስንፈው ፡ አይኖር ። ሰው ፡ የዘራውን ፡ ይለቅማል ። የሥጋ ፡ ሥራዎችን ፡ የሚዘራም ፡ ከውስጡ ፡ ጥፋትን ፡ ይለቅማል ። የመንፈስ ፡ ሥራዎችንም ፡ የሚዘራ በመንፈስ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወትን ፡ ይለቅማል ። መልካም ፡ ብንሠራም ፡ አንስነፍ ። በጊዜው ፡ እንለቅመዋለንና ። ቀን ፡ ሳለልን ፡ ለሁሉ መልካም ፡ እንሥራ ። እንግዲህ ፡ አንስነፍ ። (ገላ ፡ ፮ ፡ ፩ - ፲) ።

፩ሺ፯፻፴ ኤፌሶን ፡ ፫ ። ለተጠራችሁባት ፡ አጠራር ፡ በሚገባ ፡ በፍጹም ፡ ትኅትና ፡ በትዕግሥት ፡ በገርነትም ፡ ራሳችሁን ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ አድርጋችሁ ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ፡ እማልዳችኋለሁ ። እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ በፍቅር ፡ እየታገሣችሁ ፡ በመንፈስም ፡ ስምምነት ፡ ለመጠበቅ ፡ እየተጋችሁ ፡ በሰላምም ፡ ማሰሪያ ፡ ኑሩ ፡ አንድ ፡ ሥጋና ፡ አንድ ፡ ነፍስ ፡ ትሆኑ ፡ ዘንድ ። (ኤፌ ፡ ፬ ፡ ፩ - ፫) ።

፩ሺ፯፻፴፩ ፬ ። ፀሐይም ፡ ሳይገባ ፡ ቁጣችሁን ፡ አብርዱ። ለሰይጣንም ፡ እናንተን ፡ ለማሳት ፡ መንገድ ፡ አትስጡት ። የሚሰርቅም ፡ እንግዲህ ፡ አይሰረቅ ። ችግረኛውን ፡ በሚረዳው ፡ ገንዘብ ፡ መልካም ፡ ለመሥራት ፡ በእጆቹ ፡ ይሥራ ፡ ይድከምም ፡ እንጂ ። ግዳጃችሁ ፡ በሚፈጸም ፡ ገንዘብ ፡ ከመልካም ፡ በቀር ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ከአፋችሁ ፡ አይውጣ ። መራራውን ፡ ሁሉ ፡ ቂምን ፡ ቁጣን ፡ ጩኸትን ፡ ስድብንም ፡ ከክፋ ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ ከእናንተ ፡ አርቁ ። ባልንጀሮቻችሁንም ፡ ይቅር ፡ የምትሉ ፡ ሁኑ ። እግዚአብሔር ፡ ክርስቶስ ፡ ይቅር ፡ እንዳላችሁ ፡ ይቅር ፡ በሉ ። የተወደዳችሁ ፡ ልጆችም ፡ እንደመሆናችሁ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ምሰሉ ። ዝሙት ፡ ግን ፡ ርኩስ ፡ ሁሉ ፡ ዓመፃም ፡ በእናንተ ፡ አይሰማ ። የኀፍረት ነገርና ፡ የስንፍና ፡ ነገር ፡ የዘብብትም ፡ ነገር ፡ ጨዋታም ፡ ለቅዱሳን ፡ እንደማይገባቸው ። ይችን ፡ የማትገባ ፡ ሥራ ፡ አትቅረቡአት ። (ኤፌ ፡ ፬ ፡ ፳፯ - ፴፪ ። ፭ ፡ ፩ - ፬) ።

፩ሺ፯፻፴፪ ፊልጵስዩስ ። የደስታዬን ፡ አኳኋን ፡ ፈጽሙ። በ፩ ፡ ምክርና ፡ በ፩ ፡ ፍቅር ፡ በአንዲትም ፡ ነፍስ ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ። በማናቸውም ፡ ጠብ ፡

እዙ ፡ ወተወድሶ ፡ በከንቱ ፡ እላ ፡ በትሑት ፡ ልብ ፡ ወስያረሲ ፡ ለለ፩ዱ ፡ እምኔክሙ ፡ ቢጾ ፡ ዚአሁ ፡ ዘይኄይስ ፡ እምኔሁ ።

ክርክርንና ፡ በከንቱ ፡ መወደስን ፡ አታድርጉ ። በትሑት ፡ ልብ ፡ እንጂ ። ከእናንተ ፡ እያንዳንዱ ባልንጀራውን ፡ ከእርሱ ፡ የሚሻል ፡ ያድርግ ። (ፊል ፡ ፪ ፡ ፩ - ፯) ።

፩ሺ፮፻፹፫ መልእክተ ፡ ሐዋርያት ፡ ወዘሰ ፡ የእምር ፡ ገቢሮታ ፡ ለሠናይት ፡ ወኢይገብራ ፡ ኃጢአተ ፡ ትከውኖ ። ወእትሕቱ ፡ ርእሰክሙ ፡ ለኵሉ ፡ ፍጥረተ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ በእንተ ፡ እግዚእነ ።

፩ሺ፮፻፹፫ የሐዋርያት ፡ መልእክት ። መልካም ፡ መሥራትን ፡ የሚያውቅ ፡ የማይሠራትም ፡ ኃጢአት፡ ትሆንበታለች ። (ያዕ ፡ ፬ ፡ ፲፯) ። ስለ ፡ ጌታችን ፡ ብላችሁ ፡ ለሰው ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ራሳችሁን ፡ ዝቅ ፡ አድርጉ ፡ (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፫) ።

## አንቀጽ ፡ ፵ወ፰ቱ ፡

በእንተ ፡ ዘኮነሆሙ ፡ ለከሓድያን ፡ እምላክ ፡ ልዑል ፡ ወፀሪፍ ፡ ላዕሌሁ ። ወእምልኮተ ፡ ባዕድ ፡ ወዘይወስድ ፡ ኀቤሃ ፡ እምከዊነ ፡ ረቃዪ፡ ወመሠርይ ፡ ወስአለ ፡ ያስግሉ ፡ በፍሬ ፡ ዕፀው ፡ ወኀጠታት ፡ ወፋላት ።

፩ሺ፮፻፹፬ ምዕራፍ ፡ ቀዳማዊ ። በእንተ ፡ በእተ ፡ ክሕደት ፡ እምኔሁ ። ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ በወንጌል ፡ ጸሐፍ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እምላክከ ፡ ኪያሁ ፡ ታምልክ ፡ ወሎቱ ፡ ለባሕቲቱ ፡ ትስግድ ፡ "ወእዘዞሙ ፡ ለአርዳኢሁ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ሑሩ ፡ ወመሀሩ ፡ ኵሎ ፡ አሕዛበ ፡ ወእንዘ ፡ ታጠምቅዎሙ ፡ በሉ ፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ።" ወይቤ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ውእቱ ፡ ወይቤ ፡ አነ ፡ ወአብ ፩ዱ ፡ ንሕነ ፡ ወኵሉ ፡ ዘእቡየ ፡ ዚአየ ፡ ውእቱ ። ወዛቲ ፡ ቃል ፡ ታኤምር ፡ ከመ ፡ ይደሉ ፡ አሚነ ፡ ተዋሕዶቱ ፡ እምላካዊት ፡ ወትሥልስተ ፡ አካላቲሁ ፡ ወዕሪና ፡ አካላት ፡ በ፩ዱ ፡ ባሕርይ ፡ እምላካዊ ፡ ወሥልጣነ ፡ ዚአሁ ፡ ወዕበየ ፡ ስብሐቲሁ ።

፩ሺ፮፻፹፬ መጀመሪያ ፡ ምዕራፍ ። ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ከክህደት ፡ ስለመውጣት ፡ ይናገራል ። ጌታችን ፡ በወንጌል ፡ እንዲህ ፡ አለ ። እርስን ፡ ፈጣሪህን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ታመልክ ፡ ዘንድ ፡ ለእርሱም ፡ ብቻ ፡ ትስግድ ፡ ዘንድ ፡ ተጽፏል ። (ማቴ ፡ ፬ ፡ ፲) ። ደቀመዛሙርቱንም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ። ሂዱና ፡ አሕዛብን ፡ ሁሉ ፡ አስተምሩ ። ስታጠምቁአቸውም ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ስም ፡ በሉ ። (ማቴ ፡ ፳፰ ፡ ፲፱)። እግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ነውናም ፡ አለ ። (ዮሐ ፡ ፬ ፡ ፳፬) ። እብና ፡ እኔ ፡ አንድ ፡ ነን ። የአባቴም ፡ ገንዘብ ፡ የእኔ ፡ ነው ፡ አለ ። (ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፴) ። ይህችም ፡ ቃል ፡ አምላካዊት ፡ ተዋሕዶውን ፡ የአካላቱን ፡ ሦስትነት ፡ በአንድ ፡ አምላካዊ ፡ ባሕርይም ፡ የአካላቱን ፡ ዕሪና ፡ (እኩልነት) ፡ የእርሱን ፡ ሥልጣን ፡ የጌትነቱንም ፡ ገናናነት ፡ ማመን ፡ እንዲገባ ፡ ታመለክታለች ።

፩ሺ፮፻፹፭ ወይደሉ ፡ አምልኮ ፡ ወስጊድ ፡ ለእምላክ ፡ ባሕቲቱ ፡ እምቃለ ፡ ወንጌል ፡ ካዕበ ፡ ወእግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ቃል ፡ ወውእቱ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ወኀደረ ፡ ላዕሌነ ፡ ወርኢነ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ከመ ፡ ስብሐተ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ለእቡሁ ። ወዛቲ ፡ እማሬ ፡ በእንተ ፡ ተሠግዎቱ ፡ ለእምላክ ፡ ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ክርስቶስ ፡ ለሥልጣኑ ፡ ይደሉ ፡ ስብሐት ፡ ወለሠናይቱ ፡ ይደሉ ፡ አኰ

፩ሺ፮፻፹፭ አምልኮና ፡ ስጊድ ፡ ለአምላክ ፡ ብቻ ፡ ይገባል። ዳግመኛም ፡ ከወንጌል ፡ ቃል ። ቃልም ፡ እግዚአብሔር ፡ ነበረ ። ያም ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ሆነ ። በእኛም፡አደረ።ጌትነቱንም፡ለአባቱ፡እንደ፡አንድ ልጅ ፡ ጌትነት ፡ አየን ። (ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፩ ። ፲፬) ። ይህችም ፡ ስለአምላክ ፡ ሰው ፡ መሆን ፡ ምልክት ፡ ናት ። ይኸውም ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ። ለሥልጣኑ ፡ ክብር ፡ ይገባል ። ለቸርነቱም ፡ ምስ

እዞ ፡ ወተወድሶ ፡ በከንቱ ፡ እላ ፡ በትሑት ፡ ልብ ፡ ወለያሪሲ ፡ ለለ፩ዱ ፡ እምኔክሙ ፡ ቢጾ ፡ ዚአሁ ፡ ዘይኄይስ ፡ እምኔሁ ።

ክርክርንና ፡ በከንቱ ፡ መወደስን ፡ አታድርጉ ። በትሑት ፡ ልብ ፡ እንጂ ። ከእናንተ ፡ እያንዳንዱ ባልንጀራውን ፡ ከእርስ ፡ የሚሻል ፡ ያድርግ ። (ፊል ፡ ፪ ፡ ፩ - ፭) ።

፩ሺ፮፻፳፰ መልእክተ ፡ ሐዋርያት ፡ ወዘሰ ፡ የእምር ፡ ገቢሮታ ፡ ለሠናይት ፡ ወኢይገብራ ፡ ኃጢአተ ፡ ትከውኖ ። ወአትሕቱ ፡ ርእሰክሙ ፡ ለኵሉ ፡ ፍጥረተ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ በእንተ ፡ እግዚእነ ።

፩ሺ፮፻፳፰ የሐዋርያት ፡ መልእክት ። መልካም ፡ መሥራትን ፡ የሚያውቅ ፡ የማይሠራትም ፡ ኃጢአት፡ ትሆንበታለች ። (ያዕ ፡ ፬ ፡ ፲፯) ። ስለ ፡ ጌታችን ፡ ብላችሁ ፡ ለሰው ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ራሳችሁን ፡ ዝቅ ፡ አድርጉ ፡ (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፫) ።

## አንቀጽ ፡ ፵ወ፰ቱ ፡

በእንተ ፡ ኵነኔሆሙ ፡ ለክሓድያን ፡ አምላክ ፡ ልዑል ፡ ወበረፍ ፡ ሳዕሌሁ ። ወአምልኮተ ፡ ባዕድ ፡ ወዘይወስድ ፡ ኀቤሃ ፡ እምከዊነ ፡ ረቃዪ፡ ወመሠርይ ፡ ወለእለ ፡ ያሰግሉ ፡ በፍሬ ፡ ዕፀው ፡ ወኀጠታት ፡ ወፋላት ።

፩ሺ፮፻፳፱ ምዕራፍ ፡ ቀዳማዊ ። በእንተ ፡ በአተ ፡ ክሕደት ፡ እምኔሁ ። ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ በወንጌል ፡ ጽሑፍ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላክከ ፡ ኪያሁ ፡ ታምልክ ፡ ወሎቱ ፡ ለባሕቲቱ ፡ ትስግድ ፡ "ወአዘዞሙ ፡ ለአርዳኢሁ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ሑሩ ፡ ወመሀሩ ፡ ኵሎ ፡ አሕዛበ ፡ ወእንዘ ፡ ታጠምቅዎሙ ፡ በሉ ፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ።" ወይቤ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ውእቱ ፡ ወይቤ ፡ አነ ፡ ወአብ ፩ዱ ፡ ንሕነ ፡ ወኵሉ ፡ ዘአቡየ ፡ ዚእየ ፡ ውእቱ ። ወዛቲ ፡ ቃል ፡ ታኤምር ፡ ከመ ፡ ይደሉ ፡ እሚን ፡ ተዋሕዶቱ ፡ አምላካዊት ፡ ወትሥልስቱ ፡ አካላቲሁ ፡ ወዕሪና ፡ አካላት ፡ በ፩ዱ ፡ ባሕርይ ፡ አምላካዊ ፡ ወሥልጣነ ፡ ዚእሁ ፡ ወዕበየ ፡ ስብሐቲሁ ።

## አንቀጽ ፡ ፵፰ ።

ልዑል ፡ አምላክን ፡ ስለሚክዱ ፡ ሰዎችና ፡ እርሱንም ፡ ስለመሳደብ ፡ ጣዖትን ፡ ስለማምለክ ፡ የሚረቁና ፡ መድኀኒት ፡ አድራጊ ፡ ከመሆን ፡ የተነሣ ፡ ወደእርስዋ ፡ ስለሚወስድ ፡ በዕንጨት ፡ ፍሬና ፡ በቅንጣት ፡ በሚርትም ፡ ስለሚጠንቁሉ፡ ሰዎች ፡ ቅጣት ፡ ይናገራል ።

፩ሺ፮፻፳፱ መጀመሪያ ፡ ምዕራፍ ። ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ከክህደት ፡ ስለመውጣት ፡ ይናገራል ። ጌታችን ፡ በወንጌል ፡ እንዲህ ፡ አለ ። እርሱን ፡ ፈጣሪህን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ታመልክ ፡ ዘንድ ፡ ለእርሱም ፡ ብቻ ፡ ትሰግድ ፡ ዘንድ ፡ ተጽፏል ። (ማቴ ፡ ፬ ፡ ፲) ። ደቀመዛሙርቱንም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ። ሂዱና ፡ አሕዛብን ፡ ሁሉ ፡ አስተምሩ ። ስታጠምቁአቸውም ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ስም ፡ በሉ ። (ማቴ ፡ ፳፰ ፡ ፲፱)። እግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ነውና ፡ አለ ። (ዮሐ ፡ ፬ ፡ ፳፬) ። አብና ፡ እኔ ፡ አንድ ፡ ነን ። የአባቴም ፡ ገንዘብ ፡ የእኔ ፡ ነው ፡ አለ ። (ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፴) ። ይህችም ፡ ቃል ፡ አምላካዊት ፡ ተዋሕዶውንና ፡ የአካላቱን ፡ ሦስትነት ፡ በአንድ ፡ አምላካዊ ፡ ባሕርይም ፡ የአካላቱን ፡ ዕሪና ፡ (እኩልነት) ፡ የእርሱን ፡ ሥልጣን ፡ የጌትነቱንም ፡ ገናናነት ፡ ማመን ፡ እንዲገባ ፡ ታመለክታለች ።

፩ሺ፮፻፴ ወይደሉ ፡ አምልኮ ፡ ወሰጊድ ፡ ለአምላክ ፡ ባሕቲቱ ፡ እምቃለ ፡ ወንጌል ፡ ካዕበ ፡ ወእግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ቃል ፡ ወውእቱ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ወኀደረ ፡ ላዕሌነ ፡ ወርኢነ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ከመ ፡ ስብሐተ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ለአቡሁ ። ወዛቲ ፡ እማሬ ፡ በእንተ ፡ ተሠግዎቱ ፡ ለእምላክ ፡ ወዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ክርስቶስ ፡ ለሥልጣኑ ፡ ይደሉ ፡ ስብሐት ፡ ወለሠናይቱ ፡ ይደሉ ፡ አኰ

፩ሺ፮፻፴ አምልኮና ፡ ስጊድ ፡ ለአምላክ ፡ ብቻ ፡ ይገባል። ዳግመኛም ፡ ከወንጌል ፡ ቃል ። ቃልም ፡ እግዚአብሔር ፡ ነበረ ። ያም ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ሆነ ። በእኛም፡አደረ።ጌትነቱንም፡ለአባቱ፡አንድ፡አንድ ልጅ ፡ ጌትነት ፡ አየን ። (ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፩ ፡ ፲፬) ። ይህችም ፡ ስለአምላክ ፡ ሰው ፡ መሆን ፡ ምልክት ፡ ናት ። ይኸውም ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ። ለሥልጣኑ ፡ክብር ፡ ይገባል ። ለቸርነቱም ፡ ምስ

ቱት ። ወይቤ ፡ ልዑል ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ በው ስተ ፡ አሪት ፡ እነ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክከ ፡ ኢታምልክ ፡ ባዕደ ፡ አምላከ ፡ ዘእንበሌየ ፡ ወተ ፍጻሜቱ ፡ ዝንቱ ፡ ቃል ።

፩ሺ፮፻፴፩ ምዕራፍ ፡ ዳግም ። በእንተ ፡ ዘንኢየሙ ፡ ለለ ፩ዱ ፡ በበዚእሁ ፡ ክሒደቶሙ ፡ ወውእቱ ፡ ፪ቱ ፡ ክፍል ። ቀዳሚሁ ፡ ሥርዓተ ፡ ዘንኢ ፡ ሥጋዊ ። ትሔ ፡ ወለእመ ፡ ተንሥአ ፡ እምኔክሙ ፡ ነቢይ ፡ አው ፡ ሐላሚ ፡ ሕልም ፡ ወወሀበክሙ ፡ ትእምርተ ፡ ቃለ ፡ ጥዩቀ ፡ ወለእመ ፡ ይቤለከ ፡ ነዓ ፡ ንሑር ፡ ወናምልክ ፡ አማልክተ ፡ ካልአነ ፡ ዘኢተአምርዎሙ ፡ ኢትስምዕዎ ፡ አው ፡ ለውእቱ ፡ ነቢይ ፡ እው ፡ ለውእቱ ፡ ሐላሚ ፡ ሕልም ፡ እስመ ፡ ያሜክረክሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምላክክሙ ፡ ከመ ፡ ይርአይ ፡ ለእመ ፡ ታፈቅርዎ ፡ በኵሉ ፡ ልብክሙ ፡ ወነፍስክሙ ፡ እው ፡ አልቦ ። ወለውእቱስ ፡ ነቢይ ፡ ወሐላሚ ፡ ሕልም ፡ ቅትልዎ ፡ እስመ ፡ ነበበ ፡ ሐሰተ ፡ ላዕለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምላክክሙ ።

፩ሺ፮፻፴፪ ወለእመኒ እኁከ ፡ እስሐተከ ፡ አው ፡ ወልድከ ፡ አው ፡ ብእሲትከ፡ አው ፡ ዓርክከ ፡ ወይቤለከ ፡ በኅቡእ ፡ ነዓ ፡ ናምልክ ፡ አማልክተ ፡ ካልአነ ፡ ዘኢተእምር ፡ አንተ ፡ ወኢ ፡ እበዊከ ፡ እምእማልክተ ፡ አሕዛብ ፡ ኢትፍቅድ ፡ ዘንተ ፡ ወኢትትመከሮ ፡ እምኔሁ ወኢትኅዝን ፡ ሎቱ ፡ ወኢትሠውሮ ፡ አላ ፡ ቅትሎ ፡ በውግረተ ፡ እብን ፡ ወእደዊከ ፡ ይቅድማ ፡ ወኀሮቶ ፡ ወእደዊሆሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ሕዝብ ፡ ድኅረ ።

፩ሺ፮፻፴፫ ወለእመ ፡ ሰማዕከ ፡ በ፩ዱ ፡ እምአህጉሪከ ፡ ከመ ፡ ወፅኡ ፡ እምኔሃ ፡ ሰብእ ፡ ከሓድያን ፡ ወእስሐትዎሙ ፡ ለሰብአ ፡ ሀገሮሙ ፡ እንዘ ፡ ይብሉነሁ ፡ ናምልክ ፡ አማልክተ ፡ ባዕዳነ ፡ ዘኢተአምርዎሙ ፡ እንትሙ ፡ ኅሥሥ ፡ ጥዩቀ ፡ ዝንቱ ፡ ወተስእል ፡ በእንቲአሁ ፡ እንዘ ፡ ተሐትት ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ እሙነ ፡ ወጥዩቀ ፡ ቅትሎሙ ፡ ለሰብአ ፡ ይእቲ ፡ ሀገር ፡ በብልሐ ፡ ሰይፍ ፡ ወአጥፍእ ፡ ኪያሃ ፡ ወለኵሎሙ ፡ እለ ፡ ሀለዉ ፡ ውስቴታ ፡ ወአውዕያ ፡ በእሳት ።

፩ሺ፮፻፴፬ ትሔ ፡ ወዘሂ ፡ ይሠውዕ ፡ ለአማልክት ፡ ዘእንበለ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለይሙት ።

፩ሺ፮፻፴፭ ትሔ ፡ ወዘይሁብ ፡ እምዘርኢ ፡ ለግልፎ ፡ ይት



ጋና ፡ ይገባል ። ልዑልም ፡ ምስጋና ፡ ይግባውና፡ በኦሪት ፡ እንዲህ ፡ አለ ። እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጣሪህ ፡ ነኝ ። ከእኔ ፡ ሌላ ፡ ባዕድ ፡ አምላክ ፡ አታምልክ ። የዚህንም ፡ ቃል ፡ መጨረሻ ፡ ተና ገረ ። (ዘፀ ፡ ፳ ፡ ፫) ።

፩ሺ፮፻፴፩ ፪ኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ክህደታቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስለሆነ ፡ ስለእያንዳንዱ ፡ ቅጣት ፡ ይናገራል ። ይኸውም ፡ ሁለት ፡ ክፍል ፡ ነው ። መጀመሪያው ፡ የሥጋዊን ፡ ቅጣት ፡ ሥርዓት ፡ ይናገራል ። ትሄ ። ከእናንተ ፡ ወገን ፡ ነቢይ ፡ ወይም ፡ ሕልም ፡ የሚያልም ፡ ቢነሣ ፡ አስረጅ ፡ የሚሆን ፡ የቃል ፡ ምልክትም ፡ ቢሰጣችሁ ፡ የማታውቋቸውን ፡ ሌሎችን ፡ አማልክት ፡ ና ፡ ሂደን እናምልክ ፡ ቢልህም ፡ ያንን ፡ ነቢይ ፡ ወይም ፡ ያንን ፡ ሕልም ፡ አላሚ ፡ አትስሙት ። ፈጣሪያችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ በፍጹም ፡ ልቦናችሁና ፡ ሰውነታችሁ ፡ ትወዱት ፡ እንደሆነ ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ ይፈትናችኋልና ። ያንን ፡ ነቢይ ፡ ግን ፡ ሕልም፡አላሚውንም፡ግደሉት። በፈጣሪያችሁ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ሐሰት ፡ ተናግሯልና ።

፩ሺ፮፻፴፪ ወንድምህ ፡ ወይም ፡ ልጅህ ፡ ወይም ፡ ሚስትህ ፡ ወይም ፡ ወዳጅህ ፡ ቢያስትህ ፡ ከአሕዛብ ፡ አማልክት ፡ ወገን ፡ አንተ ፡ ወይም ፡ አባቶችህ ፡ የማታውቋቸውን ፡ አማልክት ፡ በስውር ፡ ና ፡ እናምልክ ፡ ቢልህ ፡ ይህን ፡ አትሻ ። ከእርሱም ፡ አትቀበል ። አትዘንለትም ። አትሰውረውም ። በደንጋይ ፡ ወግረህ ፡ ግደለው ፡ እንጂ ። የአንተ፡ እጆች ፡ አስቀድመው ፡ ይውገሩት ። ኋላም ፡ የሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ እጅ ።

፩ሺ፮፻፴፫ ከሀገሮችህ ፡ በአንዲቱ ፡ ከሐድያን ፡ ሰዎች ፡ ከእርስዋ ፡ ወጥተው ፡ የሀገራቸውን ፡ ሰዎች ፡ እናንተ ፡ የማታውቋቸውን ፡ ሌሎችን ፡ አማልክት ፡ ኑ ፡ እናምልክ ፡ ብለው ፡ እንዳሳቷቸው ፡ ብትሰማ ፡ የዚህን ፡ ርግጥ ፡ መርምር ። ስለእርሱ እየመረመርህ ፡ ጠይቅ ። የታመነና ፡ የተረጋገጠ ቢሆንም ፡ የዚያችን ፡ ሀገር ፡ ሰዎች ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ ግደላቸው ። ሀገሪቱንም ፡ አጥፋ ። በውስጧ ፡ ያሉትንም ፡ ሁሉ ። በእሳትም ፡ አቃጥላት ። (ዘዳ ፡ ፲፫ ፡ ፩ - ፲፯) ።

፩ሺ፮፻፴፬ ትሄ ። ለእግዚአብሔር ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ለጣዖታት ፡ መሥዋዕት ፡ የሚሠዋ ፡ ይሙት ። (ዘፀ ፡ ፳፪ ፡ ፳) ።

፩ሺ፮፻፴፭ ትሄ ። ከልጆቹ ፡ ለጣዖት ፡ የሚሰጥ ፡ በደን

ወገር ፡ በአብን ፡ ወለስብአ ፡ ሀገርኒ ፡ ለእመ ፡ ተሀየይዎ ፡ ወኢቀተልዎ ፡ እመጽአ ፡ መዓትየ ፡ ላዕሌሆሙ ። ወዘሂ ፡ ፀረፈ ፡ ላዕለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይውግርዎ ፡ በአብን ።

፩ሺ፮፻፴፮ ጠስ ፡ ፴ወ፱ቱ ፡ ወዘይብልዕ ፡ መሥዋዕተ ፡ አረሚ ፡ አው ፡ ዘያከብር ፡ ጣዖተ ፡ አው ፡ ዘይጠብሕ ፡ አው ፡ ዘየዐቀን ፡ ሎሙ ፡ ለጣኒ ፡ ይደልዎ ፡ ሥቃየ ፡ ፍትሕ ፡ ወዘከማሁ ፡ ይትኰነኑ ፡ ልጹቃኒሆሙ ፡ ወላእካኒ ፡ ምሥዋዕሂ ። ወለእለሂ ፡ ትምህርተ ፡ ካሕድ ፡ ይሜህሩ ፡ ይደልዎሙ ፡ ተፍጻሜተ ፡ ኲነኔ ፡ ወእለ ፡ ይፈልሱ ፡ እምሃይማኖቶሙ ፡ ይደልዎሙ ፡ ይረድ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ተፍጻሜተ ፡ ኲነኔ ። ወዘሂ ፡ ረከቦሙ ፡ ወኢያግብአሙ ፡ ኀበ ፡ መኳንንት ፡ ይደልዎ ፡ ተፍጻሜተ ፡ ሥቃይ ።

፩ሺ፮፻፴፯ ወጻማማዊሰ ፡ ሥርዓተ ፡ ኲነኔ ፡ መንፈሳዊ ፡ ይቤ ፡ እግዚእ ፡ በወንጌል ፡ ቅዱስ ፡ "ወዘሰ ፡ ፀረፈ ፡ ላዕለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኢይትኀደግ ፡ ሎቱ ፡ አበሳሁ ፡ በዝ ፡ ዓለም ፡ ወኢ ፡ በዘይመጽእ ፡ ዓለም" ።

፩ሺ፮፻፴፰ ወይቤ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ "መምለክያነ ፡ ጣዖት ፡ ኢይወርስዋ ፡ ለመንግሥተ ፡ እግዚአብሔር" ።

፩ሺ፮፻፴፱ ወይቤ ፡ ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ በመልእክቱ ፡ ዳግሚት ፡ ወኲሉ ፡ ዘዐለወ ፡ ትምህርተ ፡ ክርስቶስ ፡ ወኢይነብር ፡ ቦቱ ፡ አልቦቱ ፡ አምላክ ፡ ወዘሂ ፡ ይመጽእ ፡ ኀቤክሙ ፡ ወዘንተ ፡ ትምህርተ ፡ ኢያመጽእ ፡ ኢታብእዎ ፡ ቤተክሙ ፡ ወበሐሂ ፡ ጥቀ ፡ ኢትበልዎ ።

፩ሺ፮፻፵ ይቤ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ እመቦ ፡ ዘመሀረክሙ ፡ እመሂ ፡ መልአክ ፡ እምሰማይ ፡ ካልአ ፡ እምዘመሀርናክሙ ፡ ውጉዘ ፡ ለይኩን ።

፩ሺ፮፻፵፩ ዑቁ ፡ ከመ ፡ ኢይኄጡክሙ ፡ በተጥባበ ፡ ነገር ፡ ዘያዴውሁ ፡ ለክንቱ ፡ ለትምህርተ ፡ ሰብእ ፡ ፈጠራ ፡ እንተ ፡ ፈጠርዋ ፡ በመእዝነ ፡ ዓለም ፡ ወአኮ ፡ ከመ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ዘኀደረ ፡ በላዕሌሁ ፡ ኲሉ ፡ ፍጹም ፡ መለኮት ፡ በሥጋ ፡ ሰብእ ።



ጋይ ፡ ይወገር ። የሀገር ፡ ሰዎችም ፡ ቸል ፡ ቢሉት ፡ ባይገሉትም ፡ መዓቴን ፡ በላያቸው ፡ አመጣባቸዋለሁ ። እግዚአብሔርንም ፡ የተሳደበውን ፡ ሰው ፡ በደንጋይ ፡ ይውገሩት ። (ዘሌ ፡ ፳ ፡ ፪ - ፬ ። ዘዳ ፡ ፲፫ ፡ ፲) ።

፩ሺ፮፻፴፮ ጠስ ፡ ፴፱ ። የአረሚን ፡ መሥዋዕት ፡ የሚበላ ፡ ወይም ፡ ጣዖትን ፡ የሚያከብር ፡ ወይም ፡ የሚሠዋ ፡ ወይም ፡ ለጣን ፡ የሚያጥንላቸው ፡ የፍርድ ፡ ቅጣት ፡ ይገባዋል ። አለቆችንም ፡ የመሰሉ ፡ ሁሉ ፡ እንደዚሁ ፡ ይቀጡ ። የምሥዋዕ ፡ አገልጋዮችም ። የክህደት ፡ ትምህርት ፡ ለሚያስተምሩም ፡ ፍጹም ፡ ቅጣት ፡ ይገባቸዋል ። ከሃይማኖታቸውም ፡ ለሚወጡት ፡ ፍጹም ፡ ቅጣት ፡ ሊፈጸምባቸው ፡ ይገባል ። አግኝቶ ፡ ወደ ፡ መኳንንት ፡ ያላቀረባቸውም ፡ ፍጹም ፡ ቅጣት ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ፮፻፴፯ ሁለተኛው ፡ ግን ፡ የመንፈሳዊውን ፡ ቅጣት ፡ ሥርዓት ፡ ይናገራል ። ጌታ ፡ በቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ እንዲህ ፡ አለ ። መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ የሰደበ ፡ ሰው ፡ ኃጢአቱ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በሚመጣውም ፡ ዓለም ፡ አይሰረይለትም ። (ማቴ ፡ ፲፪ ፡ ፴፩ - ፴፫) ።

፩ሺ፮፻፴፰ ሐዋርያው ፡ ጳውሎስም ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ጣዖትን ፡ የሚያመልኩ ፡ ሰዎች ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ አይወርሱአትም ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፱) ።

፩ሺ፮፻፴፱ ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊም ፡ በ፪ኛ ፡ መልእክቱ ፡ እንዲህ ፡ አለ ። የክርስቶስን ፡ ትምህርት ፡ የካደ ፡ ሁሉ ፡ በእርሱ ፡ የማይኖር ፡ አምላክ ፡ በእርሱ ፡ የለም ። ወደ ፡ እናንተ ፡ የሚመጣ ፡ ይህንም ፡ ትምህርት ፡ የማያመጣ ፡ ሰውን ፡ ወደ ፡ ቤታችሁ ፡ አታስገቡት ። እንደምን ፡ አለህ ፡ እንኳ ፡ አትበሉት ። (፪ ፡ ዮሐ ፡ ፱ - ፲፩) ።

፩ሺ፮፻፵ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ካስተማርናችሁ ፡ ሌላ ፡ ያስተማራችሁ ፡ ቢኖር ፡ የሰማይ ፡ መልአክም ፡ ቢሆን ፡ የተለየ ፡ ይሁን ። (ገላ ፡ ፩ ፡ ፰) ።

፩ሺ፮፻፵፩ ፍጹም ፡ መለኮቱ ፡ ሁሉ ፡ በሰው ፡ ሥጋ ፡ እንዲያድርበት ፡ እንደ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያይደለ ፡ በመንዝነ ፡ ዓለም ፡ የፈጠሩአት ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ለሆነች ፡ ለሰው ፡ ትምህርት ፡ በከንቱ ፡ የሚያታልሉ ፡ ሰዎች ፡ እንዳያታልሉአችሁ ፡ እወቁ ። (ቈላ ፡ ፪ ፡ ፰ - ፱) ።

አንቀጽ ፡ ፵፮ ።

፩ሺ፮፻፵፪ ድስቅ ፡ ፳ወ፮ቱ ፡ ወኢይደልዎ ፡ ለክርስቲያናዊ ፡ ከመ ፡ ይገብር ፡ አስማተ፡ሆሙ ፡ ለጣዖታት ፡ ወለስይጣናት ፡ በቃለ ፡ ስባሔ ፡ ዘአ.መፍትው ፡ ወለእመ ፡ ይቤሉ ፡ ኪያሃ ፡ ይስሐብ ፡ ኀበ.ሆሙ ፡ መንፈስ ፡ ርኩስ ፡ ሀየንተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ።

፩ሺ፮፻፵፫ ጠስ ፡ ዘ፳ ፡ ወእለሂ ፡ ዘብሑ ፡ ለእማልክት ፡ ፪ተ ፡ ጊዜያተ ፡ አው ፡ ፫ተ ፡ ጊዜያተ ፡ በግብር፡ ይንበሩ ፡ ፩ተ ፡ ዓመተ ፡ በአፍአ ፡ ምስለ ፡ ዓቀብተ ፡ እንቀጽ ፡ ወእምዝ ፡ ይሳተፍዎሙ ፡ ለመሃይምናን ፡ በጸሎት ፡ ባሕቲቱ ፡ ፪ተ ፡ ዓመተ ፡ ወበሳብዕ ፡ ዓም ፡ ይትወከፍዎሙ ፡ ወይኩኑ ፡ ምስለ ፡ መሃይምናን ፡ በ፩ዱ ፡ ዕሪና ። ወቀሳውስትኒ ፡ እለ ፡ ዘብሑ ፡ ለእማልክት ፡ ወነስሑ ፡ ወኢኮነ ፡ በተመይኖ ፡ አላ ፡ በጽድቅ ፡ ወእመ ፡ ኮኑ ፡ ወገብኡ ፡ ወነስሑ ፡ ይንበሩ ፡ በክብሮሙ፡ ወኢይግበሩ ፡ ምንተኒ ፡ እምግብራተ ፡ ተክህኖ ።

፩ሺ፮፻፵፬ ዘ፪ቱ ፡ ወከማሁ ፡ ዲያቆናትኒ ፡ ወይደልዎሙ ለኤጲስቆጶሳት ፡ ከመ ፡ ያግብእዎሙ ፡ ወይፍትሑ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ በእምጣነ ፡ ገብሩ ፡ በዘይደልዎሙ ። ወተረፈ ፡ ነገርኒ ፡ በዝንቱ ፡ ፍካሬ ፡ ተነግረ ፡ በአንቀጸ ፡ ከሓድያን ።

፩ሺ፮፻፵፭ ዘ፲ወ፪ቱ ፡ ወእለሂ ፡ ዘብሑ ፡ ለግልፍዋት ፡ እምቅድመ ፡ ይጠመቁ ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ አዘዙ፡ ማኅበር፡ ከመ ፡ ይባኡ ፡ ውስተ ፡ ኍልቈ ካህናት ፡ እምድኅረ ፡ ተጠምቁ ።

፩ሺ፮፻፵፮ ዘ፫ቱ ፡ ወእለሂ ፡ ጕዩ ፡ ወተሀይዱ ፡ ንዋዮሙ፡ ወጸሩ ፡ ሥቃያተ ፡ ወውእቶሙ ፡ እንዘ ፡ ይትአመኑ ፡ ከመ ፡ መሢሓውያን ፡ እሙንቱ ፡ ወያግሀዱ ፡ ኀዘነ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ በዘገብሩ ፡ እምክሒድ ፡ በአርአያሆሙ ፡ ወበትሕትና ፡ ሑረቶሙ ፡ እሉ ፡ እሙንቱ ፡ እለ ፡ ንጹሓን ፡ እምኃጣውእ ፡ ኢትክልእዎሙ ፡ ተሳትፎ ።

፩ሺ፮፻፵፯ ዘ፮ቱ ፡ ወለእለሂ ፡ እፍርሀዎሙ ፡ በሥቃይ ፡ ወአፍለስዎሙ ፡ ወእምዝ ፡ ገብኡ ፡ በኵሉ ፡ ልበሙ ፡ ይትወከፍዎሙ ፡ ወያምፀድዎሙ ፡ ወይግበሩ ፡ ንስሓ ።

፩ሺ፮፻፵፰ ዘኒቅያ ፡ ፲ወ፩ዱ ፡ ወእለሂ ፡ ክሕዱ ፡ ዘእንበለ ፡ ዐጸባ ፡ ወኢምንዳቤ ፡ ተወክፍዎሙ ፡ ወግበሩ ፡ ሎሙ ፡ ንስሓ ፡ ጽኑዐ ።

፩ሺ፮፻፵፱ ሥርዋጽ ፡ ዘኒቅያ ፡ ፶ወ፩ቱ ፡ ወእለሂ ፡ ገብኡ፡

ስለ ፡ ከሐድያን ፡ ቅጣት ።

፩ሺ፮፻፵፪ ድስቅ ፡ ፳፮ ። ለክርስቲያን ፡ በማይገባ ፡ የምስጋና ፡ ቃል ፡ የጣዖታትንና ፡ የሰይጣናትን ፡ ስም ፡ ሊጠራ ፡ አይገባውም ። ርሱዋንም ፡ ቢጠሩ ፡ ስለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፈንታ ፡ ርኩስ ፡ መንፈስ ፡ ወደእነርሱ ፡ ይሳባል ።

፩ሺ፮፻፵፫ ጠስ ፡ ፳ ። ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ፫ ፡ ጊዜ ፡ በግድ ፡ ለጣዖት ፡ መሥዋዕት ፡ የሠዉ ፡ ሰዎች ፡ በአፍአ ፡ ከበር ፡ ጠባቂዎች ፡ ጋር ፡ ፩ ፡ ዓመት ፡ ይቆዩ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በጸሎት ፡ ብቻ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ከምእመናን ፡ ጋር ፡ ይገናኙ ። በሰባተኛው ፡ ዓመትም ፡ ይቀበሏቸው ። ከምእመናንም ጋር ፡ በ፩ ፡ እኩልነት ፡ ይኑሩ ። ለጣዖት ፡ መሥዋዕት ፡ የሚሠዉ ፡ ቀሳውስትም ፡ ቢጸጸቱም ፡ በእውነት ፡ እንጂ ፡ በተንኰል ፡ ባይሆን ፡ ተመልሰው ፡ የተጸጸቱ ፡ ቢሆኑ ፡ በክብራቸው ፡ ይኑሩ ። ከክህነት ፡ ሥራዎች ፡ ወገን ፡ ምንም ፡ አይሥሩ ።

፩ሺ፮፻፵፬ ፪ ። ዲያቆናትም ፡ እንደዚሁ ፡ ናቸው ። ለኤጲስቆጶሳትም ፡ በሚገባቸው ፡ በሠሩት ፡ ልክ ፡ ፈርደው ፡ ይመልሱአቸው ፡ ዘንድ ፡ ይገባቸዋል። በዚህ ፡ ትርጓሜ ፡ ከተነገረው ፡ የቀረውም ፡ በአንቀጸ ፡ ከሓድያን ፡ ተነግሯል ። (ፍ ፡ ነ ፡ ፻፶፺፯ - ፻፻፷፩) ።

፩ሺ፮፻፵፭ ፲፪ ። ጥምቀተ ፡ ክርስትናን ፡ ከመጠመቃቸው ፡ በፊት ፡ ለጣዖት ፡ የሠዉ ፡ ሰዎች ፡ ከተጠመቁ ፡ በኋላ ፡ ከካህናት ፡ ቍጥር ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ ማኅበር ፡ አዝዘዋል ።

፩ሺ፮፻፵፮ ፫ ። የተሰደዱ ፡ ገንዘባቸውንም ፡ የተቀሙ ፡ እነርሱ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደሆኑ ፡ አምነው ፡ መከራ ፡ የተቀበሉም ፡ ሰዎች ፡ ከክህደት ፡ ወገን ፡ ባደረጉት ፡ ነገር ፡ ማዘናቸውን ፡ በሁኔታቸው ፡ በአካሄዳቸውም ፡ ትሕትና ፡ ቢገልጹ ፡ ከኃጢአት ፡ የነጹ ፡ እሊህ ፡ ናቸው ። አንድነትን፡ አትከልክሉአቸው ።

፩ሺ፮፻፵፯ ፮ ። በሥቃይ ፡ አስፈራርተው ፡ ያሳደዱአቸውም ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በፍጹም ፡ ልቡናቸው ፡ ቢመለሱ ፡ ይቀበሏቸው ። ይምከሩአቸውም ። ንስሓም ፡ ያድርጉ ።

፩ሺ፮፻፵፰ ኒቅያ ፡ ፲፩ ። ያለ ፡ ጭንቅና ፡ መከራ ፡ የካዱትንም ፡ ሰዎች ፡ ተቀበሏቸው ። ጽኑ ፡ ንስሓም ፡ ያድርጉ ።

፩ሺ፮፻፵፱ ሥርዋዕ ። ኒቅያ ፡ ፶፩ ። በሆነ ፡ ሆኖ ፡ ከሃይማ

እምሃይማኖቶሙ ፡ በዘኮነ ፡ ከዊኖ ፡ እመዓርግ ፡ ለይረዱ ፡ እምኔሃ ፡ ኀበ ፡ ዘይቴሐት ።

፩ሺ፯፻፶፱ ምዕራፍ ፡ ሣልስ ፡ በእንተ ፡ ፍትሐ ፡ ዘነኔ ፡ በበይነ ፡ ዘይወስድ ፡ ኀበ ፡ እምልኮ ፡ ካልእ ፡ ዘኢኮነ ፡ እምላከ ፡ ከመ ፡ እምሳከ ፡ ልዑል ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ዘከመ ፡ ረቃዪ ፡ ወመሠርይ ፡ ወተጠይሮ ፡ በእንጽፎ ፡ ሐመድ ፡ ወፍሬ ፡ ዕፀው ፡ ወሐመር ፡ ወበቀልት ፡ ወሕጠታተ ፡ ዛጐል ፡ ወፋል ።

፩ሺ፯፻፷፩ ትቤ ፡ ወለመሠርይ ፡ ኢታሕይዎ ። መጅ ፡ ብእሲኒ ፡ ወብእሲትኒ ፡ እመቦ ፡ ዘኮኑ ፡ ሐራስያን ፡ እው ፡ ዘሥራይ ፡ ሞተ ፡ ለይሙቱ ፡ ወበእብን ፡ ለይውግርዎሙ ፡ እስመ ፡ ጊጉያን ፡ እሙንቱ ፡ ወደሞሙ ፡ ዲበ ፡ ርእሶሙ ።

፩ሺ፯፻፷፪ ትሔ ፡ ወኢይትረከብ ፡ በውስቴትክሙ ፡ ዘየኀሥሥ ፡ ትምህርተ ፡ ሐረሳውያን ፡ ወማእምራን ፡ ወእ. ፡ ዘያደሉ ፡ ለገጽ ፡ ወእ. ፡ መሠርይ ፡ ወኢ ፡ ዘይጤየር ፡ ወኢ ፡ ዘይረቂ ፡ ርቅየተ ፡ ወኢዘይሴእሎሙ ፡ ለስብእ ፡ ሐረስ ፡ ወኢ ፡ ለመንቅሕያን ፡ ምዉት ፡ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ዘይገብር ፡ ዘንተ ፡ ግብረ ፡ ርኩስ ፡ ውእቱ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምላክክሙ ።

፩ሺ፯፻፷፫ ረስጣ ፡ ፳ወ፱ቱ ፡ ረስጣ ፡ ፷ወ፫ቱ ፡ መሠርይ ፡ ወዘይጤየር ፡ ዲበ ፡ እንጽፎ ፡ ሐመድ ፡ ወፍሬ ፡ ዕፀው ፡ ወሕጠታተ ፡ ዛጐል ፡ ወመንቅሕያን ፡ ምዉት ፡ ወመፈክራነ ፡ አሕላም ፡ ወስብአ ፡ ፋል ፡ ወገባርያነ ፡ ኰርበታት ፡ ይኅድጉ ፡ ወእመ ፡ እኮ ፡ ይሰደዱ ።

፩ሺ፯፻፷፬ዘኒቅያ ፡ ፳ወ፪ቱ ፡ ወኢይሳተፍ ፡ ፩ዱ ፡ እመሃይምናን ፡ ምስለ ፡ መሠርያን ፡ ወማእምራን ፡ ወዘገብረ ፡ ዘንተ ፡ ወተሳተፎሙ ፡ ወዘይሴአሎሙ ፡ ወያጸድቅ ፡ ቃሎሙ ፡ ወዘሂ ፡ ያበውአሙ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡ ወቦአ ፡ ቤቶሙ ፡ ወበልዐ ፡ እክሎሙ ፡ ወሰትየ ፡ ስቴሆሙ ፡ እመሂ ፡ ኮነ ፡ እምካህናት ፡ ለይደቅ ፡ እመዓርጊሁ ፡ ወይክልእዎ ፡ እምትድምርተ ፡ መሃይምናን ፡ ወእመሂ ፡ ኮነ ፡ እምሕዝባውያን ፡ ይትገኀሥ ፡ እምተደምሮቶሙ ፡ ወለእመ ፡ ነስሐ ፡ የሀብዎሙ ፡ ንስሓ ።



ኖታቸው ፡ የተመለሱ ፡ ሰዎች ፡ ከመዓርጋቸው ፡ ወደ ፡ ዝቅተኛ ፡ መዓርግ ፡ ይውረዱ ።

፩ሺ፯፻፶፱ ፫ኛ ፡ ምዕራፍ ። ምስጋና ፡ ይግባውና ፡ እንደ ፡ ልዑል ፡ አምላክ ፡ አምላክ ፡ ወደ ፡ አልሆነ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ ስለሚወስድ ፡ ስለቅጣት ፡ ፍርድ ፡ ይናገራል ። ይኸውም ፡ እንደሚረጭ ፡ ሥራይ ፡ እንደሚያደርግ ፡ አመድ ፡ በመነስነስ ፡ በእንጨት ፡ ፍሬ ፡ በተረር ፡ ቃሞ ፡ በስሌን ፡ በዛጎል ፡ ቅንጣት ፡ በጥንቆላ ፡ እንደማሚረት ፡ ያለ ፡ ነው ።

፩ሺ፯፻፷፩ ትቤ ። መሠርይን ፡ አታድነው ። (ዘጸ ፡ ፳፪ ፡ ፲፰) ። መጅ ። ወንድና ፡ ሴትም ፡ ሟርተኞች ፡ ወይም ፡ መሠርዮች ፡ ቢሆኑ ፡ ሞትን ፡ ይሙቱ ። በደንጋይም ፡ ይውገሩአቸው ። በደለኞች ፡ ናቸውና ። ደማቸውም ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ ነው ።

፩ሺ፯፻፷፪ ትሂ ። የሟርተኞችንና ፡ የጠንቋዮችን ፡ ትምህርት ፡ የሚሻ ፡ ወይም ፡ ፊት ፡ እይቶ ፡ የሚያደላ ፡ ወይም ፡ መሠርይ ፡ ወይም ፡ የሚያሟርት ፡ ወይም ፡ መርጨትን ፡ የሚረጭ ፡ ወይም ፡ የሟርት ፡ ሰዎችንና ፡ ሙት ፡ አንሽዎችን ፡ የሚጠይቃቸው ፡ በውስጣችሁ ፡ አይገኝ ። ይህን ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፡ ሁሉ ፡ በፈጣሪያችሁ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ርኩስ ፡ ነውና ። (ዘዳ ፡ ፲፰ ፡ ፱-፲፪)።

፩ሺ፯፻፷፫ ረስጣ ፡ ፳፱ ። ረስጣ ፡ ፷፫ ። ሥር ፡ የሚምስ ፡ አመድ ፡ የእንጨት ፡ ፍሬ ፡ የዛጎል ፡ ቅንጣትም ፡ በመበተን ፡ የሚያሟርት ፡ ሙት ፡ የሚያስነሡም ፡ ሕልም ፡ ተርጓሚዎችም ፡ የጥንቈላ ፡ ሰዎች ፡ ክታብ ፡ አድራጊዎችም ፡ ይተዉ ። ባይተዉ ፡ ይሰደዱ ።

፩ሺ፯፻፷፬ ኒቅያ ፡ ፳፪ ። ከምእመናን ፡ አንዱ ፡ ከመሠርያንና ፡ ከጠንቋዮች ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ አይሁን ። ይህንም ፡ ያደረገ ፡ የተቀላቀላቸው ፡ የሚጠይቃቸው ፡ ቃላቸውንም ፡ እውነት ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ወደቤቱም ፡ የሚያስገባቸው ፡ ወደቤታቸውም ፡ የገባ ፡ እህላቸውን ፡ የበላ ፡ መጠጣቸውንም ፡ የጠጣ ፡ ከካህናት ፡ ወገን ፡ ቢሆን ፡ ከሹመቱ ፡ ይሻር ። ከምእመናንም ፡ አንድነት ፡ ይከልከሉት ። ከሕዝባውያን ፡ ወገን ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ከአንድነታቸው ፡ ይራቅ ። ቢመለሱም ፡ ንስሓ ፡ ይስጧቸው ።

## አንቀጽ ፡ ፵ወ፯ቱ ፡

በእንተ ፡ ቀቲል ፡ ወኵንኔሁ ፡ ሥጋዊ ፡ ወመንፈሳዊ ፡ ዘተነግረ ፡ በቀኖናሁ ።

፩ሺ፮፻፶፫ ቀቲልሰ ፡ እምኍልቈ ፡ ዐበይት ፡ ኃጣውእ ፡ ክልኤት ፡ ወውጉዛት ፡ በልብ ፡ ወበሕግ ፡ ወኢይትፌጸም ፡ ዝንቱ ፡ ዘእንበለ ፡ በቀቲለ ፡ ሥጋ ፡ ወበእውፅአተ ፡ ነፍስ ፡ በኵነኔ ፡ ሥጋዊ ፡ እምነበ ፡ መኰንን ፡ ሥጋ ፡ ከመ ፡ ይትፈጸም ፡ ሕግ ፡ ሥጋዊ ። ወእመኒ ፡ ኢተከሥተ ፡ ይኩን ፡ ኵነኔሁ ፡ መንፈሳዊ ፡ እምነበ ፡ መኰንን ፡ ነፍሳት ፡ ዘውእቱ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ከመ ፡ ይርከብ ፡ ድኅነ ፡ እምኵነኔ ፡ ዘይረክቦ ፡ በዓለም ፡ ዘኢየኀልፍ ።

፩ሺ፮፻፶፬ ወቀቲልኒ ፡ ይትከፈል ፡ ኀበ ፡ ፪ቱ ፡ አክፋል ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘኢይደልዎ ፡ ኵነኔ ። ጠስ ፡ ፴ወ፱ቱ ፡ ወውእቱ ፡ ዝንቱ ፡ ዘእልቦቱ ፡ ልብ ፡ ወለዘኢፈድፈደ ፡ መዋዕሊሁ ፡ እም፯ቱ ፡ ዓመታት ፡ ወለሰካሬኒ ፡ በእንተ ፡ ዘኮነ ፡ ኵነኔሁ ፡ ከመ ፡ ዘእልቦቱ ፡ ልብ ፡ ኢይደልዎ ፡ ቀቲል ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ እጥፍእ ፡ ልቦ ፡ በሥምረተ ፡ ዚእሁ ፡ ወለዕቡድሰ ፡ ወዝንጉሰ ፡ ይጠፍእ ፡ ልቦሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ሥምረቶሙ ፡ ወኢይኩን ፡ ኵነኔሁ ፡ ከመ ፡ ኵነኔሆሙ ። ወልብኒ ፡ ይፌትሕ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ እመ ፡ ኮነ ፡ ልሙደ ፡ በሰኪር ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ በተሃርብዮ ፡ ኢይከውን ፡ ኵነኔሁ ፡ ከመ ፡ ኵነኔሆሙ ፡ ወፈድፋደሰ ፡ ለእመ ፡ ቀተለ ፡ በሰካሩ ፡ ምዕረ ፡ ዳግመ ፡ እው፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ማእከሌሁ ፡ ወማእከለ ፡ ቅቱል ፡ ባእስ ፡ እምቀዲሙ ።

፩ሺ፮፻፶፭ ወለእመ ፡ ኢኮነ ፡ ስዉረ ፡ በተሃርብዮ ፡ ወኀልቦ ፡ ባእስ ፡ ማእከሌሆሙ ፡ ይትኰነን ፡ በኵነኔ ፡ ሰካርያን ፡ ወይኩን ፡ ኵነኔሁ ፡ ከመ ፡ ኵነኔሁ ፡ ለዘቀተለ ፡ ዘእንበለ ፡ ፈቃዱ ።

፩ሺ፮፻፶፮ ወለዘሂ ፡ እንበረኒ ፡ ከመ ፡ ይቅትል ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘአንበሮ ፡ መኰንን ፡ ውእቱ ፡ ላዕለ ፡ ሥጋ ፡ አልቦ ፡ ሰዳ ፡ በላዕሌሁ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ካልእ ፡ አግዚ ፡ ሥሉጥ ፡ ላዕለ ፡ ተአግዚ ፡ ይደሉ ፡ ኵነኔሁ ፡ ላዕለ ፡ እግዚኡ ። ወእመሰ ፡ ኢኮነ ፡ ሥሉጠ ፡ በላዕሌሁ ፡ ወኢይፈርህ ፡ እምኔሁ ፡ ይደሉ ፡ ኵነኔሁ ፡ ላዕለ ፡ ተእግዚ ።

፩ሺ፮፻፶፯ ወካልእ ፡ ክፍል ፡ ዘይደሉ ፡ ኵነኔ ፡ በላዕሌሁ ፡ በዘይመጽእ ፡ ጥዩቀሁ ፡ ወውእቱ ፡ ካልእ ፡ እም



## አንቀጽ ፡ ፵፯ ።

ስለ ፡ መግደልና ፡ በአንቀጹ ፡ ስለተነገረ ፡ ሥጋዊና ፡ መንፈሳዊ ፡ ቅጣቱ ፡ ይናገራል ።

፩ሺ፮፻፶፫ መግደልስ ፡ በልብና ፡ በሕግ ፡ ከተከለከሉት ፡ ከተለዩትም ፡ ከታላላቁ ፡ ኃጣውእ ፡ ቍጥር ፡ ነው ። ይህም ፡ ሥጋዊ ፡ ሕግ ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ከሥጋዊ ፡ ዳኛ ፡ ዘንድ ፡ በሥጋዊ ፡ ፍርድ ፡ ሥጋን ፡ በመግደልና ፡ ነፍስን ፡ በማውጣት ፡ (በማዳን) ፡ካልሆነ ፡ በቀር ፡ አይፈጸምም ። ባይገለጽም ፡ መንፈሳዊ ፡ ቅጣቱ ፡ ከነፍሳት ፡ ዳኛ ፡ ዘንድ ፡ ይሁን ። ይኸውም ፡ የካህናት ፡ አለቃ ፡ ነው ። በማያልፈው ፡ ዓለም ፡ ከሚያገኘው ፡ ቅጣት ፡ ይድን ፡ ዘንድ ።

፩ሺ፮፻፶፬ መግደልም ፡ ከሁለት ፡ ክፍል ፡ ይከፈላል ። ከእነርሱም ፡ አንዱ ፡ ቅጣት ፡ የማይገባው ፡ (የማያስቀጣ) ፡ ነው ። ጠስ ፡ ፴፱ ። ይኸውም ፡ እእምሮ ፡ የሌለው ፡ ነው ። ዘመኑም ፡ ከ፯ ፡ ዓመት ፡ ላልበዛ ፡ ለሰካራምም ፡ ፍርዱ ፡ እእምሮ ፡ እንደሌለው ፡ ሰው ፡ ስለሆነ ፡ ሞት ፡ አይገባውም ። ርሱ ፡ በፈቃዱ ፡ እእምሮውን ፡ አጥፍቷልና ። ለሰብድና ፡ ለዝንጉዕ ፡ ግን ፡ አእምሯቸው ፡ ያለፈቃዳቸው ፡ ይጠፋል ። ቅጣቱም ፡ እንደ ፡ ቅጣታቸው ፡ አይሁን ። እርሱ ፡ በስካር ፡ የለመደ ፡ እንደሆነም ፡ ልብ ፡ ይፈርዳል ። በመንደላቀቅ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ቅጣቱ ፡ እንደ ፡ ቅጣታቸው ፡ አይሆንም ። ይልቁንም ፡ በመስከሩ ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ቢገድል ፡ ወይም ፡ በሚችና ፡ በገዳይ ፡ መካከል ፡ ከጥንት ፡ ጠብ ፡ ቢኖር ፡

፩ሺ፮፻፶፭ በመቀማጠል ፡ (በመንደላቀቅ) ፡ የታወቀ ፡ ካልሆነ ፡ በመካከላቸውም ፡ ጠብ ፡ ባይኖር ፡ በሰካራሞች ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣ ። ቅጣቱም ፡ ያለ ፈቃዱ ፡ እንደገደለ ፡ ሰው ፡ ቅጣት ፡ ይሁን ።

፩ሺ፮፻፶፮ እንዲገድል ፡ ለአስገደዱት ፡ ሰው ፡ ያስገደደው ፡ ሥጋዊ ፡ ዳኛ ፡ ቢሆን ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ሰዳ ፡ የለበትም ። ሌላው ፡ አዛዥ ፡ በታዛዡ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ቢሆን ፡ ቅጣቱ ፡ ለአዛዡ ፡ ይገባል ። በእርሱ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ባይሆን ፡ ግን ፡ ከእርሱም ፡ የተነሣ ፡ የማይፈራ ፡ ቢሆን ፡ ቅጣቱ ፡ ለታዛዡ ፡ ይገባል ።

፩ሺ፮፻፶፯ ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ በሚመጣው ፡ መረጃ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ የሚገባውን ፡ ቅጣት ፡ ይናገ

ዘቀደመ ፡ ዘከርነ ፡ ።

፩ሺ፮፻፺ ወቀትልሰ ፡ ላዕለ ፡ ፪ቱ ፡ አክፋል ፡ ፩ዱ ፡ እም ኔሆሙ ፡ ዘእልቦቱ ፡ ተማኅጸ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወቀ ትል ፡ ወባሕቱ ፡ ትእዛዝ ። ወውእቱ ፡ ፪ቱ ፡ አክፋል ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ በእንተ ፡ ዘኢያፈ ቅድ ፡ ቀቲለ ፡ ወይከውን ፡ ቀትል ፡ እምተእን ትሎ ፡ ወ፩ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘያፈቅድ ፡ ቀቲለ ፡ ወይትገኃሥ ፡ እምተሠጥዎተ ፡ ቅትለቱ ።

፩ሺ፮፻፺፩ ትቤ ፡ ለእመ ፡ ተረክበ ፡ ሰረቃ ፡ ውስተ ፡ ክርየተ ፡ ቤት ፡ ወዘበጥዎ ፡ ወሞተ ፡ አልቦ ፡ ዕዳ ፡ ላዕለ ፡ ቀታሊሁ ፡ ወእመሰ ፡ ሠረቀ ፡ በሐይ ፡ ላዕሌሁ ፡ ይደልዎ ፡ ሞት ፡ ለቀታሊሁ ።

፩ሺ፮፻፺፪ ጠስ ፡ ፴ወ፱ቱ ፡ ወለፈያታዊስ ፡ ይደሉ ፡ ከሉ ፡ ለለ፩ዱ ፡ ፩ዱ ፡ ከመ ፡ ይቅትሎ ፡ ለእመ ፡ ክነ ፡ ዘኢይትከሀሎ ፡ ይድኅን ፡ እምኔሁ ፡ ዘእንበለ ፡ ሕሠም ፡ ዘይረክባ ፡ ለነፍሱ ።

፩ሺ፮፻፺፫ ዘሣወ፬ቱ ፡ ወአልቦ ፡ ዕዳ ፡ ከሰበ ፡ ላዕለ ፡ ዘይቀትል ፡ ብእሴ ፡ ዘመጽአ ፡ ኀበ ፡ ቤቱ ፡ ሌሊተ ፡ ለአሕሥሞ ፡ በእንተ ፡ ተዓቅቦ ፡ እንበ ይነ ፡ ሕይወተ ፡ ነፍሱ ።

፩ሺ፮፻፺፬ ዘ፲ወ፱ቱ ፡ ወሰብእ ፡ ጽልእ ፡ እለ ፡ ይጸብኡ ፡ ወእለሂ ፡ ጕዩ ፡ ኀቤሆሙ ፡ በሰይፍ ፡ ይትቀተሉ ፡

፩ሺ፮፻፺፭ ዘሣወ፪ቱ ፡ ወዘይእኅዞ ፡ ለዘዘመወ ፡ ምስለ ፡ ብእሲቱ ፡ ለእመ ፡ ተጻደቆ ፡ ወቀተሎ ፡ ኢይ ደሉ ፡ ላዕሌሁ ፡ ኵነኔ ፡ ቀታሊ ፡ ወዘሐመዮ ፡ ለብእሲ ፡ በእርኵሶተ ፡ ንጽሕ ፡ ለብእሲቱ ፡ ወነ ገረ ፡ ፫ተ ፡ ጊዜያተ ፡ ወፈነወ ፡ ዘይነግሮ ፡ ዘንተ ፡ በቅድመ ፡ ስማዕታት ፡ ምእመናን ፡ ወለእመ ፡ ተረክበ ፡ ምስሌሃ ፡ እመሂ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡ እው ፡ ውስተ ፡ ቤታ ፡ እው ፡ በመካነ ፡ ስታይ ፡ እው ፡ በመካነ ፡ ነዋቢ ፡ ብሩር ፡ ወቀ ተሎ ፡ ምተ ፡ ዚአሃ ፡ በእዴሁ ፡ ኢይረክቦ ፡ ዕዳ ። ወለእመ ፡ ረከቦ ፡ በካልእ ፡ መካን ፡ እው ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይመጥዎ ፡ ለሊቀ ፡ ዘይ ፈትሕ ፡ ላዕለ ፡ ኃጣውእ ፡ ወለእመ ፡ ሞዖ ፡ በቅ ድሜሁ ፡ በስምዐ ፫ቱ ፡ ይደሉ ፡ ላዕሌሁ ፡ ፍትሐ ፡ ዘማውያን ።

፩ሺ፮፻፺፮ ዳግም ፡ በእንተ ፡ አግብርት ፡ ወዘመድ ፡ ለአ ግብርትስ ፡ ፪ቱ ፡ ቃላት ፡ ንቡራን ፡ በእንቲአ ሆሙ ። ቀዳማዊ ፡ ትቤ ፡ ዘ፩ዱ ፡ ወለእመ ፡ ዘበጠ ፡ ፩ዱ ፡ ገብሮ ፡ እው ፡ እመቶ ፡ በበትር ፡



ገራል ። ይህም ፡ አስቀድሞ ፡ ከተነገረው ፡ ሌላ ፡ ነው ።

፩ሺ፮፻፺ መግደልስ ፡ ሁለት ፡ ክፍል ፡ ነው ። ከእነርሱም አንዱ ፡ ቅጣትና ፡ ሞት ፡ የሌለበት ፡ ነው ። ነገር ግን ፡ ትእዛዝ ፡ ነው ። እርሱም ፡ ፪ ፡ ክፍል ፡ ነው ከእነርሱም ፡ መግደልን ፡ ስለማይወድና ፡ ከቸ ልተኝነት ፡ የተነሣ ፡ ስለሚሆነው ፡ መግደል ፡ ነው ። ከእነርሱም ፡ አንዱ ፡ መግደልን ፡ የወ ደደ ፡ ለመግደልም ፡ መልስ ፡ ከመስጠት ፡ የራቀ ነው ።

፩ሺ፮፻፺፩ ትቤ ፡ ሌባ ፡ ቤት ፡ በመቆፈር ፡ ቢገኝና ፡ ደብ ደበውት ፡ ቢሞት ፡ በገዳዩ ፡ ዕዳ ፡ የለበትም ። በሐይ ፡ ብትወጣበት ፡ ግን ፡ ለገዳዩ ፡ ሞት ፡ ይገባዋል ። (ዘፀ ፡ ፳፪ ፡ ፪ - ፬) ።

፩ሺ፮፻፺፪ ጠስ ፡ ፴፱ ። ሽፍታን ፡ ግን ፡ እንዱም ፡ እንዱ ፡ ሁሉ ፡ ሊገለው ፡ ይገባል ። ሰውነቱን ፡ ከሚያገኘት ፡ ጥፋት ፡ በቀር ፡ ከእርሱ ፡ ሊድን ፡ የማይቻለው ፡ ከሆነ ።

፩ሺ፮፻፺፫ ሣ፬ ። ዳግመኛም ፡ ከፉ ፡ ለመሥራት ፡ በሌ ሊት ፡ ወደቤቱ ፡ የመጣውን ፡ ሰው ፡ ነፍሱን ፡ ስለማዳን ፡ በመጠበቅ ፡ በገደለው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ዕዳ ፡ የለበትም ።

፩ሺ፮፻፺፬ ፲፱ ። የሚዋጉ ፡ የሰልፍ ፡ ሰዎች ፡ ወደእነርሱ ም ፡ የሸሹ ፡ በሰይፍ ፡ ይደብደቡ ።

፩ሺ፮፻፺፭ ሣ፪ ። ከሚስቱ ፡ ጋር ፡ የሚሰስነውን ፡ የያ ዘው ፡ ሰው ፡ በድንገት ፡ አግኝቶ ፡ ቢገድለው ፡ የገዳይ ፡ ቅጣት ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ አይገባም ። የሚስቱን ፡ ንጽሕና ፡ በማርከስ ፡ ሰውን ፡ ያማ ፡ ሰው ፡ ፫ ፡ ጊዜ ፡ ቢነግረው ፡ በታመኑ ፡ ምስክ ሮች ፡ ፊት ፡ ይህን ፡ የሚነግረው ፡ ቢልክም ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከእርስዋ ፡ ጋራ ፡ ሲነጋገር ፡ ቢገኝ ፡ በቤቱ ፡ ወይም ፡ በእርሱዋ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በመጠጥ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በብር ፡ እንጥረኛ ፡ ቤት ፡ ቢሆን ፡ ባሏም ፡ በእጁ ፡ ቢገ ድለው ፡ ዕዳ ፡ አያገኘውም ። በሌላ ፡ ቦታ ፡ ወይም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቢያገኘው ፡ በወ ንጀል ፡ ለሚፈርድ ፡ ዳኛ ፡ ይስጠው ። በዳኛ ውም ፡ ፊት ፡ በሦስት ፡ ምስክር ፡ ቢረታው ፡ የዘማውያን ፡ ፍርድ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ይገባል ።

፩ሺ፮፻፺፮ ፪ኛው ፡ ስለባሮችና ፡ ስለዘመዶች ፡ ይናገ ራል ። ለባሮችስ ፡ ስለእነርሱ ፡ የተጻፉ ፡ ሁለት ፡ አሉ ። መጀመሪያው ፡ ትቤ ፡ ፩ ። አንድ ፡ ሰው ፡ ወንድ ፡ ባሪያውን ፡ ወይም ፡ ሴት

ወሞተ ፡ ታሕተ ፡ እዴሁ ፡ ይትኰነን ፡ በኰነኔሁ ። ወለእመስ ፡ ሐይወ ፡ አሐደ ፡ ዕለተ ፡ አው ፡ ፪ተ ፡ ኢይትኰነን ፡ እስመ ፡ ንዋየ ፡ ዚእሁ ፡ ውእቱ ።

፩ሺ፰፻፳፯ ጠስ ፡ ፴፱ቱ ፡ ወዘቀሠፈ ፡ ፩ደ ፡ እምእግብርቲሁ ፡ በእነዳ ፡ አው ፡ በበትር ፡ ወኮነ ፡ በዝንቱ፡ ሞተ ፡ ዚእሁ ፡ ኢይፍትሕ ፡ ላዕሌሁ ፡ ፍትሐ ፡ ቀታሊ ። ወለእመስ ፡ ኮነ ፡ ዘቀሠፎ ፡ አብዝኀ ፡ ቀሢፎቶ ፡ አው ፡ ቀተሎ ፡ በሕምዝ ፡ አው ፡ አውዐዮ ፡ በእሳት ፡ ይትኰነን ፡ ኰነኔ ፡ ቀታሊ ።

፩ሺ፰፻፳፰ ወቀል ፡ ዳግማዊ ፡ መክ ፡ ፶ወ፩ቱ ፡ ወእመቦ ፡ ዘቦቱ ፡ ገብር ፡ ዘአበሰ ፡ አበሳ ፡ ዘይደሉ ፡ ለቀቲል ፡ ያብጽሖ ፡ ለውእቱ ፡ ገብር ፡ እግዚአ ፡ ኀበ ፡ መኳንንት ፡ ከመ ፡ ይኰንንዎ ፡ በአበሳሁ ፡ ወለእመስ ፡ ተኀበለ ፡ ላዕለ ፡ ቀቲሎቱ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ሥልጣን ፡ አው ፡ ዘኢኮነ ፡ ብዉሐ ፡ ቦቱ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ይደሉ ፡ ላዕሌሁ ፡ ፍትሐ ቀትል ።

፩ሺ፰፻፳፱ ወበእንተ ፡ እዝማድስ ፡ ፬ ፡ ፱ቱ ፡ ቃላት ፡ ቀዳማዊ ፡ ትሔ ፡ ኢይቅትልዎሙ ፡ ለአበው ፡ ህየንተ ፡ ውሉዶሙ ፡ ወኢለውሉድ ፡ ህየንተ ፡ አበዊሆሙ ።

፩ሺ፰፻፴ ወዳግማዊ ፡ ጠስ ፡ ፴፱ቱ ፡ ዘይቀትል ፡ አዝማዲሁ ፡ እምአበዊሁ ፡ ላዕለ ፡ ወእምውሉድ ፡ ዘበታሕቱ ፡ ወቅሩባኒሁ ፡ ይመጥውዎ ፡ ለኰነኔ ። ወቦ ፡ ካልእ ፡ ፍኖ ፡ ዘይደሉ ፡ ላዕሌሁ ፡ ኰነኔ ፡ ዘኢ ፡ ይኤዝዝ ፡ ከመ ፡ ይቅትሎ ፡ አው ፡ ዘለሊሁ ፡ ገብረ ።

፩ሺ፰፻፴፩ ወለአባዚስ ፡ ጠስ ፡ ፴፱ቱ ፡ ወብእሲ ፡ ዘይኤዝዝ ፡ ሰብአ ፡ ከመ ፡ ይቅትል ፡ ይፍትሑ ፡ ላዕሌሁ ፡ ፍትሐ ፡ ቀታሊ ፡ ወተባረኒ ፡ ዘይትኤዘዝ ፡ ሎቱ ፡ እመኒ ፡ በትምይንት ፡ ኀብአት ፡ ዘከመ ፡ ሕምዝ ፡ ወሥራይ ፡ ወአውዕዮ ፡ በእሳት ። ጠስ ፡ ፴፱ቱ ፡ እስመ ፡ ይወስድዎ ፡ በኰነኔ ፡ ቀታልያን ፡ ለዘኒ ፡ ይገብር ፡ ሕምዘ ፡ ለቀቲለ ፡ ሰብእ ፡ አው ፡ ለዘሀሎ ፡ ኀቤሁ ፡ ሕምዝ ፡ ወይሠይጥ ፡ ኪያሁ ።

፩ሺ፰፻፴፪ ወእመቦ ፡ እግዚእ ፡ አው ፡ ገብር ፡ በምንትኒ ፡ ፍኖት ፡ እምፍናዋት ፡ ዘወሀበ ፡ ሎቱ ፡ ሕምዘ ፡ እመሂ ፡ ብእሲት ፡ ለብእሲሃ ፡ አው ፡ ብእሲ ፡

ባሪያውን ፡ በበትር ፡ ቢመታና ፡ በእጁ ፡ ቢሞት በቅጣቱ ፡ ይቀጣ ። (በገደለበት ፡ ይሙት) ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ደኅና ፡ ቢሆን ፡ አይቀጣ ። ገንዘቡ ፡ ነውና ። (ዘፀ ፡ ፳፩ ፡ ፳ - ፳፪) ።

፩ሺ፰፻፳፯ ጠስ ፡ ፴፱ ። ከባሮቹ ፡ አንዱን ፡ በአለንጋ ፡ ወይም ፡ በአርጩሜ ፡ (በጨንገር) ፡ የገረፈ ፡ ሰው ፡ ሞቱም ፡ በዚህ ፡ ቢሆን ፡ የገዳይ ፡ ፍርድ፡ አይፍረዱበት ። ገራፊው ፡ አብዝቶ ፡ የገረፈው፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ በመርዝ ፡ ቢገድለው ፡ ወይም፡ በእሳት ፡ ቢያቃጥለው ፡ በገዳይ ፡ ቅጣት ፡ ይቀጣ ።

፩ሺ፰፻፳፰ ሁለተኛው ፡ ነገር ፡ መክ ፡ ፶፩ ። ለሞት ፡ የሚያበቃ ፡ በደል ፡ የበደለ ፡ ባሪያ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ በቅጣቱ ፡ ይቀጡት ፡ ዘንድ ፡ ጌታው ፡ ያንን ፡ ባሪያ ፡ ከዳኞች ፡ ያድርሰው ። ሥልጣን ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የማይገባው ሰው ፡ እርሱን ፡ ለመግደል ፡ ቢደፍር ፡ ግን ፡ ስለዚህ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ይገባል ።

፩ሺ፰፻፳፱ ስለ ፡ ዘመዶችስ ፡ ፪ ፡ ፍርዶች ፡ አሉ ። መጀመሪያው ፡ ትሄ ። አባቶችን ፡ ስለልጆቻቸው ፡ ፈንታ ፡ ልጆችንም ፡ ስለአባቶቻቸው ፡ ፈንታ ፡ አይግደሉአቸው ። (ዘዳ ፡ ፳፬ ፡ ፲፮) ።

፩ሺ፰፻፴ ጠስ ፡ ፴፱ ። ወደላይ ፡ ከአባቱ ፡ ወገን ፡ ዘመዶቹን ፡ ከልጆቹም ፡ ወገን ፡ ወደታች ፡ ያሉትን ፡ ቅርብ ፡ ዘመዶቹንም ፡ የገደለውን ፡ ሰው ፡ ለቅጣት ፡ ይስጡት ። በእርሱም ፡ ላይ ፡ ቅጣት ፡ የሚገባ ፡ ሌላ ፡ መንገድ ፡ አለ ። እንዲገድሉ ፡ የሚያዝዝ ፡ ወይም ፡ እርሱ ፡ ይህን ፡ ቢያደርግ ።

፩ሺ፰፻፴፩ ለአዛዥስ ፡ ጠስ ፡ ፴፱ ። እንዲገድል ፡ ሰውን የሚያዝዝ ፡ ሰው ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ የገዳይ ፡ ፍርድ ፡ ይፍረዱበት ። የሚታዘዝለት ፡ አድራጊውም ፡ በተሸሸገች ፡ ተንኮልም ፡ ቢሆን ፡ ይኸውም ፡ እንደመርዝና ፡ እንደ ፡ ሥራይ ፡ በእሳትም ፡ እንደማቃጠል ፡ ያለ ፡ ነው ። ጠስ ፡ ፴፱ ። በነፍስ ፡ ገዳዮች ፡ ቅጣት ፡ ይወስዱታልና ፡ ሰውን ፡ ለመግደል ፡ መርዝ ፡ የሚያዘጋጅ ፡ ወይም ፡ መርዝ ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ ለአለው ፡ እርሱንም ፡ ለሚሸጥ ።

፩ሺ፰፻፴፪ ጌታ ፡ ወይም ፡ ባሪያ ፡ ከሥራ ፡ በማናቸውም፡ ሥራ ፡ የመርዝ ፡ መጠጥ ፡ የሰጠ ፡ ቢኖር ፡ ሴት ፡ ለባሏ ፡ ወይም ፡ ባል ፡ ለሚስቱ ፡ ሴት ፡ ባሪያ ፡

ለብእሲቱ ፡ እው ፡ እመት ፡ ለእግዝእታ ፡ እው ፡ ገብር ፡ ለእግዚኡ ፡ ወሐመ ፡ እምዝንቱ ፡ ግብር ፡ ወዘእስተየ ፡ ሰብ ፡ ለቢጹ ፡ ወሞተ ፡ ይትከሎነኑ ፡ በመጥባሕት ።

፩ሺ፮፻፸፫ ወእለ ፡ ይጼውዑ ፡ አጋንንተ ፡ ለቀቲለ ፡ ሰብእ ፡ ይትከሎነኑ ፡ በሰይፍ ፡ እመሰ ፡ ገብሩ ፡ ዘንተ ፡ በኢያእምሮቶሙ ፡ ይሰደዱ ፡ ወይኑ ስሑ ።

፩ሺ፮፻፸፬ ቀኖናሁሰ ፡ ለውስዩተ ፡ እሳት ፡ ናሁ ፡ ተነ ግረ ፡ ወዘክሡትስ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ አክፋል ፡ ውእቱ ፡

፩ሺ፮፻፸፭ ቀዳማዊ ፡ ለእመ ፡ ፈተደ ፡ ይቅትል ፡ ብእሴ ፡ በገሃድ ፡ ወቀተሎ ። መጀ ፡ ወዘቀተለ ፡ ብእሴ ፡ በግፍዕ ፡ ይትቀተል ፡ ህየንቴሁ ፡ ወዝንቱ ፡ ፍትሕ ፡ ይኩን ፡ ለኩሎሙ ።

፩ሺ፮፻፸፮ ትቢ ፡ ወኮሉ ፡ ብእሲ ፡ ዘዘበጠ ፡ ብእሴ ፡ ወሞተ ፡ ለይቅትልዎ ፡ ህየንቴሁ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ልሙደ ፡ ወተማኅፀነ ፡ በምሥዋዕ ፡ ንሥ እዎ ፡ እምህየ ፡ ወቅትልዎ ።

፩ሺ፮፻፸፯ መክ ፡ ፶ወ፫ቱ ፡ ወዘእቀሰሎ ፡ ፩ዱ፯ ፡ ለካ ልእ ፡ በኀጺን ፡ እው ፡ ዘበጠ ፡ በእብን ፡ እው ፡ በዕፅ ፡ ከመ ፡ ይሙት ፡ ወእምዝ ፡ ሞተ ፡ ይደ ልዎ ፡ ለውእቱ ፡ ቀታሊ ፡ ይትቀተል ፡ ህየን ቴሁ ። ወእመሰ ፡ መሐርዎ ፡ አዝማዲሁ ፡ ለቅ ቱል ፡ ይደሉ ፡ ካዕሊሁ ፡ ፍትሐ ፡ ንስሓ ፡ ጥዩቀ ፡ ለዓለም ፡ ወባሕቱ ፡ በእንተ ፡ ተመይጦቱ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይምሐርዎ ፡ በንስሓ ።

፩ሺ፮፻፸፰ ክፍል ፡ ዳግማዊ ፡ ዘይፈቅድ ፡ ቀቲለ ፡ ብእሲ እሙር ፡ ወእምዝ ፡ ቀተለ ፡ ብእሴ ፡ ካልእ ፡ ዘኢ ኮነ ፡ ይፈቅድ ፡ ቀትሎ ፡ ዘኢሁ ፡ ይትፌታሕ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ እመ ፡ ኮነ ፡ ብእሲ ፡ ዘመፍቀዱ ፡ ቀቲል ። ወምክንያቱስ ፡ ይፈትሕ ፡ ከመ ፡ እመ ፡ ዘኮነ ፡ ይፈቅድ ፡ ቀቲሎቶ ፡ ይደሉ ፡ ተማኅጽ ፡ ካዕለ ፡ ቀታሊሁ ፡ ወይኩውን ፡ ፍትሑ ፡ ካዕለ ፡ ዘተቀትለ ፡ ከመ ፡ ይፍትሑ ፡ ለዘድኅነ ፡ ሶበ ፡ ይቀትልዎ ። ለእመሰ ፡ ኢተጠየቀ ፡ ይኩን ፡ ፍት ሑ ፡ ፍትሐ ፡ ዘቀተለ ፡ ዘእንበለ ፡ ፈቃዱ ፡ ወናሁ ፡ ተነግረ ፡ በተፍጻሜተ ፡ አንቀጽ ።

፩ሺ፮፻፸፱ ክፍል ፡ ሣልስ ፡ ለእመ ፡ ዘበጠ ፡ ፩ዱ ፡ ብእሲ ካልአ ፡ በንዋይ ፡ ዘዐቢ ፡ ይክውን ፡ ቀትል ፡ ወሞያ ፡ ዘከመ ፡ ንዋየ ፡ ሐቅል ፡ ወእእባን ፡ እንዘ ፡ ኢይፈቅድ ፡ ቀቲሎቶ ፡ ወቀተሎ ።



ለእመቤቷ ፡ ወይም ፡ ወንድ ፡ ባሪያ ፡ ለጌታው ፡ ቢሆን ፡ ከዚህ ፡ ሥራ ፡ የተነሣ ፡ ቢታመም ፡ ለባልንጀራውም ፡ መርዝ ፡ አጠጥቶት ፡ ቢሞት ፡ በሰይፍ ፡ ይቀጡ ።

፩ሺ፮፻፸፫ ሰውን ፡ ለመግደል ፡ ጋኔን ፡ የሚስቡ ፡ በሰ ይፍ ፡ ይቀጡ ። ይህን ፡ ባለማወቃቸው ፡ ቢሠ ሩት ፡ ግን ፡ ይለዩ ። ንስሐም ፡ ይግቡ ።

፩ሺ፮፻፸፬ በእሳት ፡ የማቃጠል ፡ ፍርድ ፡ ግን ፡ እነሆ ፡ ተነገረ ። የተገለጸውስ ፡ ፲፪ ፡ ክፍል ፡ ነው ።

፩ሺ፮፻፸፭ መጀመሪያው ፡ ሰውን ፡ በግልጥ ፡ ሊገድል ፡ ወድዶ ፡ ቢገድለው ፡ መጅ ። ሰውን ፡ በግፍዕ ፡ የገደለ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ እርሱ ፡ ፈንታ ፡ ይሙት ። ይህም ፡ ፍርድ ፡ ይጽናላችሁ ።

፩ሺ፮፻፸፮ ትቢ ። ሰውን ፡ የመታ ፡ ሰው ፡ ቢሞትም ፡ ስለእርሱ ፡ ፈንታ ፡ ይግደሉት ። የለመደም ፡ ቢሆን ፡ በመሠውያውም ፡ ቢማፀን ፡ ከዚያ ፡ ወስዳችሁ ፡ ግደሉት ። (ዘፀ ፡ ፳፩ ፡ ፲፪ - ፲፬) ።

፩ሺ፮፻፸፯ መክ ፡ ፶፫ ። አንዱ ፡ ሌላዉን ፡ በብረት ፡ ቢያቆስለው ፡ ወይም ፡ በደንጋይ ፡ ወይም ፡ በዕን ጨት ፡ እንዲሞት ፡ ቢመታው ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ቢሞት ፡ ገዳዩ ፡ ስለእርሱ ፡ ፈንታ ፡ ሊሞት ፡ ይገባዋል ። የሟች ፡ ወገኖች ፡ ይቅር ፡ ቢሉት ፡ ግን ፡ የታወቀ ፡ የንስሐ ፡ ፍርድ ፡ ለዘለዓለም ፡ ለእርሱ ፡ ይገባል ። ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ስለመመለሱ ፡ በንስሓ ፡ ይቅር ፡ ይበ ሉት ። (ንስሓዉን ፡ ያቅልሉለት) ።

፩ሺ፮፻፸፰ ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ የታወቀ ፡ ሰውን ፡ ለመ ግደል ፡ የሚወድ ፡ ሰው ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ያል ወደደውን ፡ ሌላውን ፡ ሰው ፡ ቢገድል ፡ መግ ደል ፡ ፈቃዱ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ከሆነ ፡ እንደዚ ያው ፡ ይፈረድበት ። መግደሉን ፡ የሚሻ ፡ ከሆነ ፡ ግን ፡ በገዳዩ ፡ ላይ ፡ ቅጣት ፡ እንደሚ ገባ ፡ አስተያየት ፡ (ልቡና) ፡ ይፈርዳል ። የተገደ ለው ፡ ሰው ፡ ፍርድ ፡ በሚገድሉት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ዳነ ፡ ሰው ፡ ፍርድ ፡ ይሆናል ። ባይረጋገጥ ፡ ግን ፡ ፍርዱ ፡ ያለፈቃዱ ፡ እንደ ፡ ገደለ ፡ ሰው ፡ ፍርድ ፡ ይሁን ። በአንቀጹ ፡ መጨረሻም ፡ እነሆ ፡ ተነግሯል ።

፩ሺ፮፻፸፱ ፫ኛ ፡ ክፍል ። አንድ ፡ ሰው ፡ ለሞት ፡ በሚያ ደርስ ፡ በሌላ ፡ መሣሪያ ፡ ቢመታና ፡ ቢያደክ መው ፡ ያኸውም ፡ እንደ ፡ በር ፡ መሣሪያ ፡ እንደ ፡ ደንጊያ ፡ ያለ ፡ ነው ። መግደሉንም ፡

፩ሺ፮፻፹ ጠስ ፡ ፵ወ፱ቱ ፡ ዘይዘብጦ ፡ ለ፩ዱ ፡ በሰይፍ ፡ ወለእመ ፡ ቀተሎ ፡ ይትቀተል ፡ በሰይፍ ፡ ወእመሰ ፡ ኢሞተ ፡ ዘተዘብጠ ፡ ይዎትሩ ፡ እዴሁ ፡ ለዘባጢ ፡ እስመ ፡ ይፈረ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ይስፋሕ ፡ እዴሁ ፡ ለመቲር ፡ በሰይፍ ። ወለእመ ፡ ተዳደቁ ፡ ተባእስ ፡ ማእከለ ፡ ሰብእ ፡ ወሞተ ፡ ፩ዱ ፡ ብእሲ ፡ በውስቴታ ፡ ለይትረአይ ፡ ንዋይ ፡ ዘቦቱ ፡ ተቀትለ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ በትረ ፡ ገዚፈ ፡ አው ፡ እብነ ፡ ዐቢየ ፡ አው ፡ ዘይከውን ፡ እምኔሁ ፡ ከዊነ ፡ ቀትል ፡ ይፍትሑ ፡ ቦቱ ። ወለእመሰ ፡ ኮነ ፡ ቀቲል ፡ በዘይቀልል ፡ እምኔሃ ፡ ይገብዎሙ ፡ ወይስድድዎሙ ።

ሳይወድድ ፡ ቢገድለው ።

፩ሺ፮፻፹ ጠስ ፡ ፵፱ ። አንዱን ፡ በሰይፍ ፡ የሚመታው ፡ ቢገድለውም ፡ በሰይፍ ፡ ይገደል ። የተመታው ፡ ባይሞት ፡ ግን ፡ የተማቹን ፡ እጁን ፡ ይቈረጡት ። በሰይፍ ፡ ለመቍረጥ ፡ እጁን ፡ ሲዘረጋ ፡ ደፍሯልና ። በሰዎች ፡ መካከል ፡ ድንገት ፡ ጠብ ፡ ቢነሣ ፡ አንድ ፡ ሰውም ፡ በውስጢ ፡ ቢሞት ፡ የሞተበት ፡ መሣሪያ ፡ ይታይ ። ወፍራም ፡ በትር ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ታላቅ ፡ ደንጋይ ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ከእነርሱ ፡ የተነሣ ፡ የሞት ፡ ሁኔታ ፡ የሚሆንበት ፡ ቢሆን ፡ ይፍረዱበት ። ሞቱ ፡ ከእነርሱዋ ፡ በሚቀልል ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ገርፈው ፡ ይስደዷቸው ።

፩ሺ፮፻፹፩ ክፍል ፡ ራብዕ ፡ ወለእመ ፡ ኮነት ፡ ዛቲ ፡ ዝብጠት ፡ ኀበ ፡ ብእሲ ፡ ካልእ ፡ ዘኢኮነ ፡ ይፈቅድ ፡ ቀቲሎቶ ፡ ወቀተሎ ፡ ወዝንቱ ፡ ለእመ ፡ ተማኅፀነ ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይድኅን ፡ ወእመ ፡ አኮሰ ፡ ፈታሒ ፡ ይፍታሕ ፡ ማእከሌሆሙ ፡ ወይዕርቆ ፡ ምስለ ፡ ሰብአ ፡ ደሙ ። ወዝንቱ ፡ ገከ፡ ፡ በክፍል ፡ ዳግማዊ ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ኢገብረ ፡ በእንተ ፡ ቀቲል ፡ ወባሕቱ ፡ ፈቀደ ፡ ዝብጠተ ፡ ወተቀትለ ፡ በስሕተት ፡ ወለእመ ፡ አልቦ ፡ ዕርቅ ፡ ይደልዎ ፡ ስደት ።

፩ሺ፮፻፹፩ አራተኛ ፡ ክፍል ። ይህች ፡ አመታት ፡ ሊገድለው ፡ ወደአልወደደው ፡ ወደሌላ ፡ ሰው ፡ ብትሆን ፡ ቢገድለውም ፡ እርሱም ፡ በቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቢማፀን ፡ ይድናል ። ይህም ፡ ባይሆን ፡ ዳኛ ፡ በመካከላቸው ፡ ፈርዶ ፡ ከባለደሞቹ ፡ ጋራ ፡ ያስታርቀው ። ይህም ፡ በሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ተነግሯል ። እርሱ ፡ ስለመግደል ፡ አላደረገውምና ። ነገር ፡ ግን ፡ መማታትን ፡ ወድዶ ፡ በስሕተት ፡ ሞተበት ። ዕርቅም ፡ ባይኖር ፡ ስደት ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ፮፻፹፪ ክፍል ፡ ኃምስ ፡ ለእመ ፡ ዘበጦ ፡ በንዋይ ፡ ዘኢይከውን ፡ ቦቱ ፡ ቀትል ፡ ዝብጠተ ፡ ብዙኀ ፡ በዕፀው ፡ አው ፡ በእንዳ ፡ ላሕም ፡ እንዘ ፡ ኢይፈቅድ ፡ ቀቲሎቶ ፡ ወቀተሎ ፡ ወዝንቱ ፡ ቃል ፡ ይደመር ፡ ኀበ ፡ ቃል ፡ ቀዳማዊ ፡ ዘተነግረ ፡ በፍትሐ ፡ አግብርት ። ወእመሰ ፡ ዘበጦ ፡ በሐብል ፡ አው ፡ በበትር ፡ ቀሊል ፡ ወኮነ ፡ እምነ ፡ ዝንቱ ፡ ምክንያተ ፡ ሞቱ ፡ ኢይፍትሑ ፡ ላዕሌሁ ፡ ፍትሐ ፡ ቀታሊ ። ወእመሰ ፡ ዘበጦ ፡ ዝብጠተ ፡ ብዙኀ ፡ እንበለ ፡ ምሕክ ፡ ይደልዎ ፡ ኮነኔ ፡ ቀታሊ ።

፩ሺ፮፻፹፪ አምስተኛ ፡ ክፍል ፡ ሊገድለው ፡ ሳይወድ ፡ ሞት ፡ በማይሆንበት ፡ መሣሪያ ፡ በእርጩሜ ፡ ወይም ፡ በአለንጋ ፡ መላልሶ ፡ መምታትን ፡ ቢመታውና ፡ ቢገድለው ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ በባሮች ፡ ፍርድ ፡ በተነገረው ፡ በመጀመሪያው ፡ ቃል ፡ ይጨመራል ። በገመድ ፡ ወይም ፡ በቀላል ፡ በትር ፡ ቢመታው ፡ ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ የሞቱ ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፡ የገዳይ ፡ ፍርድ ፡ አይፍረዱበት ። ያለርኅራኄ ፡ ብዙ ፡ አመታት ፡ ቢመታው ፡ ግን ፡ የገዳይ ፡ ቅጣት ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ፮፻፹፫ ክፍል ፡ ሳድስ ፡ ወእመሰ ፡ ወድቀት ፡ ዛቲ ፡ ዝብጠት ፡ ኀሊፋ ፡ ኀበ ፡ ካልእ ፡ ወቀተለቶ ፡ ወዝንቱ ፡ ፍትሑ ፡ ይኩን ፡ ከመ ፡ ፍትሕ ፡ ራብዓዊ ፡ እስመ ፡ ዝንቱ ፡ ይቀልል ፡ ወይንእስ ፡ እምኔቱ ፡ ግብረት ፡ ወኔቱ ፡ ዝብጠታት ፡ ዘተጽሕፉ ፡ ቅድመ ።

፩ሺ፮፻፹፫ ስድስተኛ ፡ ክፍል ። ይህች ፡ በትር ፡ አልፋ ፡ ከሌላ ፡ ሳይ ፡ ብትወድቅና ፡ ብትገድለው ፡ ይህ፡ ፍርድ ፡ እንደ ፡ አራተኛው ፡ ክፍል ፡ ፍርድ ፡ ይሁን ። ይህ ፡ አስቀድመው ፡ ከተጻፉት ፡ ከሁለቱ ፡ ሥራዎችና ፡ ከሁለቱ ፡ አመታቶች ፡ ይቀላልና ።

፩ሺ፮፻፹፬ ክፍል ፡ ሳብዕ ፡ ለእመ ፡ ዘበጠ ፡ ዝብጠተ ፡ ንዋይ ፡ ንኡስ ፡ ዘኢይከውን ፡ ቦቱ ፡ ቀትል ፡ እንዘ ፡ ይትጋተብ ፡ ከመ ፡ ለወረዛ ፡ ግዑይ ፡ ይዘ

፩ሺ፮፻፹፬ ፯ኛ ፡ ክፍል ። ጨነኛውን ፡ ጎልማሳ ፡ ወደ ፡ ሞት ፡ ወሰን ፡ በማያደርስ ፡ በእጅ ፡ ወይም ፡ በትንሽ ፡ በትር ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እንደሚመቱት ፡ እየ

ብዙኃ ፡ በእድ ፡ አው ፡ በበትር ፡ ንስቲት ፡ ብዙኅ ፡ ጊዜያተ ፡ ዘኢይበጽሕ ፡ ኅበ ፡ ዓቅመ ፡ ቀትል ፡ ወኮነ ፡ በዝንቱ ፡ ምክንያተ ፡ ሞቱ ፡ አው ፡ ይመውት ፡ በካልእ ፡ ዘከማሁ ፡ እው ፡ ኀለፈ ፡ ዝብጠት ፡ ኅበ ፡ ካልእ ፡ ወቀተለ ። ጠስ፡ ፵ወ፱ቱ ፡ ለእመ ፡ ዘበጠ ፡ ፩ዱ ፡ በጊዜ ፡ ጽልእ ፡ በእደዊሁ ፡ ወቀተሎ ፡ ይትዐበዮ ፡ ወይስድድዎ።

፩ሺ፯፻፹፮ ክፍል ፡ ሳምን ፡ ወዘሂ ፡ ይፈቅድ ፡ ተባውዖ ፡ ከመ ፡ ዘይገፍዖ ፡ ብእሲ ፡ ለብእሲ ፡ ኅበ ፡ ማይ ፡ እው ፡ እመልዕልት ፡ ኅበ ፡ መትሕት ፡ አው ፡ እንዘ ፡ ያፈርህ ፡ በሰይፍ ፡ ወይከውን ፡ በዝንቱ ፡ ምክንያተ ፡ ሞቱ ፡ አው ፡ ይመውት ፡ በካልእ ፡ ዘከማሁ ፡ ወዝኒ ፡ ፍትሕ ፡ ይከውን ፡ ከመ ፡ ቀዳሚ ።

፩ሺ፯፻፹፯ ክፍል ፡ ታስዕ ፡ ወበቱ ፡ ብእሲ ፡ ዘኢይፈቅድ ፡ ቀቲለ ፡ ብእሲ ፡ ወኢይፈቱ ፡ ዘበጠ ፡ እላ ፡ እንዘ ፡ ይፈቱ ፡ ግብረ ፡ ካልእ ፡ ከመ ፡ ዘይፈቅድ ፡ ዘቢጠ ፡ እንስሳ ፡ እው ፡ ከመ ፡ ዘይነድፍ ፡ በሐፅ ፡ ለቅትለተ ፡ አራዊት ፡ ለእመ ፡ ቀተለ ፡ ሰብእ ፡ ወዝንቱሰ ፡ ኅበ ፡ ፪ቱ ፡ እክፋል ፡ ይትከፈል ።

፩ሺ፯፻፹፰ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ለእመ ፡ ይትዐወቅ ፡ ከዊን ፡ ቀትል ፡ በመካነ ፡ ንስወት ፡ ለእመ ፡ ወረወ ፡ ከመ ፡ ዘይዊሩ ፡ ዖፈ ፡ አው ፡ አርዌ ፡ በማእከለ ፡ ሰብእ ፡ አው ፡ በማእከለ ፡ ሀገር ፡ ዘየኀድሩ ፡ ውስቴታ ፡ ወውእቱ ፡ እንዘ ፡ ኢይፈቅድ ፡ ቀቲለ ፡ ሰብእ ፡ ኢ ፡ በቀዳሚ ፡ ወኢ ፡ በደኃሪ ፡ ወተቀትለ ፡ ብእሲ ፡ በዝንቱ ፡ ምክን ያት ፡ ይኩን ፡ ፍትሑ ፡ ከመ ፡ ፍትሐ ፡ ዘኢገብረ ፡ በፈቃዱ ፡ በእንተ ፡ ተዓውቆቱ ፡ በመካነ ፡ ንዒው ። ዝኒ ፡ የሐጽጽ ፡ እምከዊነ ፡ ቀቲል በእንተ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ኢፈቀደ ፡ ቀቲለ ፡ ሰብእ ።

፩ሺ፯፻፹፱ ወከማሁ ፡ ዘአጥረየ ፡ አረፍተ ፡ ጽኑዓ ፡ አው፡ ገብረ ፡ ዘእኩይ ፡ ግእዙ ፡ እው ፡ እንስሳ ፡ እለ ፡ ይቀትሉ ፡ ወአብቅልተ ፡ እለ ፡ ይረግዙ ፡ አው ፡ አግማለ ፡ ሠራርያነ ፡ እው ፡ እባዕረ ፡ እለ ፡ ይወግዙ ፡ ለእመ ፡ ኢዐቀበ ፡ ወኢነገረ ፡ ከመ ፡ ይት ዓቀቡ ። አው ፡ ዘይከረ ፡ ዓዘቅተ ፡ ውስተ ፡ ፍኖት ፡ ወኢይከድኖ ፡ አው ፡ ዘይገብር ፡ ተሥላላተ ፡ ወኢየዐቅቦን ። ወናሁ ፡ ተነግረ ፡ በአሪት ፡ በፍጻሜ ፡ ምዕራፍ ፡ ዘተደመረ ፡ ምስለ ፡ አብጥሊስ ፡ ወውእቱ ፡ ዘ፴ወ፰ቱ ፡ ወውስተ ፡

ተጠንቀቀ ፡ ሞት ፡ በማይሆንበት ፡ በቅንሽ ፡ መሣሪያ ፡ መምታትን ፡ ቢመታው ፡ የሞቱም ፡ ምክንያት ፡ በዚህ ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ በእንደዚህ፡ ባለ ፡ በሌላ ፡ ቢሞት ፡ ወይም ፡ በትሩ ፡ ወደ ፡ ሌላ አልፎ ፡ ቢገድል ፡ ጠስ ፡ ፵፱ ። አንዱ ፡ በጥል ፡ ጊዜ ፡ በቡጢ ፡ ቢመታውና ፡ ቢገድለው ፡ ገር ፈው ፡ ይስደዱት ።

፩ሺ፯፻፹፮ ስምንተኛ ፡ ክፍል ። ጨዋታን ፡ የወደደ ፡ ሰው ፡ አንዱ ፡ አንዱን ፡ ወደውኃ ፡ ወይም ፡ ከላይ ፡ ወደታች ፡ ቢገፋው ፡ ወይም ፡ በሰይፍ ፡ ሲያስፈራራው ፡ በዚህ ፡ የሞቱ ፡ ምክንያት ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ በእንደዚህ ፡ ባለ ፡ በሌላ ፡ ቢሞት ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ ሥራ ፡ በሌላው ፡ ቢሆን፡ ይህ ፡ ፍርድ ፡ እንደፊተኛው ፡ ይሆናል ።

፩ሺ፯፻፹፯ ዘጠኘኛ ፡ ክፍል ። ሰው ፡ መግደልንና ፡ መማ ታትን ፡ የማይወድ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ ሲሻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንስሳ ፡ ለመምታት ፡ እን ደሚሻ ፡ ወይም ፡ አውሬ ፡ ለመግደል ፡ ቀስት ፡ እንደሚወረውር ፡ ሰውን ፡ ቢገድል ፡ ይህ ፡ ከሁለት ፡ ክፍል ፡ ይከፈላል ።

፩ሺ፯፻፹፰ ከእነዚህም ፡ አንዱ ፡ አገዳደሉ ፡ በአደን ፡ ቦታ ፡ መሆኑ ፡ ቢታወቅ ፡ በሰዎች ፡ መካከል ፡ ወይም ፡ በሚኖርባት ፡ በመንደር ፡ መካከል ፡ ለዖፍ ፡ ወይም ፡ ለአውሬ ፡ እንደሚወረውር ፡ ቢወረውር ፡ ይኸውም ፡ በፊትም ፡ ሆነ ፡ በኋላ ፡ ሰውን ፡ ለመግደል ፡ ሳይሻ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ሰው ፡ ቢሞት ፡ በአደን ፡ ቦታ ፡ መሆኑ ፡ ስለታ ወቀ ፡ ፍርዱ ፡ ወድዶ ፡ እንደ ፡ አላደረገ ፡ ሰው ፡ ፍርድ ፡ ይሁን ። ይህም ፡ ሰው ፡ መግደልን ፡ ስለአልወደደ ፡ ከአገዳደል ፡ ሁኔታ ፡ ያንሣል ።

፩ሺ፯፻፹፱ ሊናድ ፡ የተቃረበ ፡ ግንብን ፡ ወይም ፡ ጠባዩ ፡ ክፉ ፡ የሆነ ፡ ባሪያ ፡ ወይም ፡ የሚገድሉ፡ ከብቶችን ፡ የሚራገጡ ፡ በቅሎችን ፡ ወይም ፡ ዘለው ፡ የሚራገጡ ፡ ግመሎችን ፡ ወይም ፡ የሚ ዋጉ ፡ በሬዎችን ፡ ገንዘብ ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፡ ባይ ጠብቅ ፡ እንዲጠነቀቁ ፡ ባይናገርም ፡ ወይም ፡ በጐዳና ፡ ዳር ፡ ጉድጓድ ፡ ቆፍሮ ፡ ባይከድነው ፡ ወይም ፡ ሰገነት ፡ የሠራ ፡ ሰው ፡ ባይጠነቀቅባ ቸው ፡ እነሆ ፡ ከአብጥሊስ ፡ ጋራ ፡ በተጨመ ረው ፡ በኦሪት ፡ በመጨረሻው ፡ ምዕራፍ ፡ ሁኑ

## እንቀጽ ፡ ዘይኤምር ፡ ኀበ ፡ ዝንቱ ።

፩ሺ፮፻፹፱ ወዳግም ፡ ለእመ ፡ ኢተዐውቀ ፡ ከዊነ ፡ ቀትል ፡ ከመ ፡ ዘይዘብጥ ፡ እንስሳ ፡ ወይዘብጦ ፡ ለብእሲ ፡ ዘኢርእየ ፡ ኪያሁ ፡ አው ፡ ይርኅየ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ አው ፡ ዘያወድቅ ፡ ቦቱ ፡ አረፍተ ፡ ዘኢሐሰበ ፡ በድቀተ ፡ ዚአሁ ፡ አው ፡ ለእመ ፡ እልቦቱ ፡ ግብር ፡ ወኢእንስሳ ፡ እማሳንያን ፡ ወኢዓዘቅት ፡ በፍኖት ፡ ወኢተሥዕሉ ፡ ንሥተ ፡ ለዘባጢስ ፡ ወለዘይደረቢ ፡ ዘንኡሰሙ ፡ ይኩን ፡ ተሰዶ ። ለገብርስ ፡ ወለእንስሳ ፡ ይንሥአሙ ፡ በዓለ ፡ ደም ፡ ወለበዓለ ፡ ጠፈርስ ፡ አው ፡ ለበዓለ ፡ ዓዘቅት ፡ አው ፡ ለበዓለ ፡ አረፍት ፡ ኢይረክቦሙ ፡ ዕዳ ፡ ምንትኒ ።

፩ሺ፮፻፺ ክፍል ፡ ዓሥር ፡ ዘይቀትሎ ፡ ለብእሲ ፡ ወይከልእ ፡ በጺሐ ፡ ኀበ ፡ ረቀዳቲሁ ፡ ወከልእ ፡ ከመ ፡ ኢይበጽሑ ፡ ኀቤሁ ፡ ከመ ፡ ይሙት ፡ ወሞተ ፡ በረኃብ ፡ አው ፡ ዘያንድዮ ፡ በአእምሮቱ ፡ ምስለ ፡ ዘይቀትል ፡ ወቀተሎ ፡ ዘከመ ፡ አንበሳ ፡ ወከመ ፡ ከይሲ ፡ ወለዝንቱስ ፡ ፍትሑ ፡ ከመ ፡ ዘቀተለ ፡ በአእምሮቱ ።

፩ሺ፮፻፺፩ ክፍል ፡ ፲ወ፩ዱ ፡ ኩሉ ፡ ዘይከውን ፡ ስምዐ ፡ ላዕለ ፡ ብእሲ ፡ በእንተ ፡ ሞት ፡ ወቀተልዎ ፡ ወእምድኅረዝ ፡ ሶበ ፡ ተዐውቀ ፡ ከመ ፡ በሐሰት ፡ ስምዐ ፡ ኮነ ፡ ይትቀተል ፡ ዝንቱ ፡ ብእሲ ፡ በከመ ፡ ተነግረ ፡ በኦሪት ፡ ወበቀኖናት ። ለዝኒ ፡ ቀደመ ፡ ዘከርቱ ፡ ውስተ ፡ አንቀጸ ፡ ስምዕ ፡ ወይዴመር ፡ ምስሌሁ ፡ ኩሉ ፡ ዘይከውን ፡ ፈታሒ ፡ ወይፈትሕ ፡ በሞት ፡ ወይትቀተል ፡ ብእሲ ፡ ወይትዐወቅ ፡ እምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ከመ ፡ ፈትሐ ፡ በዓመፃ ፡ እንዘ ፡ የአምር ፡ ሐሰተ ፡ ስማዕት ፡ ላዕለ ፡ ቅቱል ፡ አው ፡ ዘይመስሎ ፡ ለዝንቱ ።

፩ሺ፮፻፺፪ ክፍል ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ከመ ፡ ኢይፍትሑ ፡ በገቢረ ፡ ቀትል ፡ ላዕለ ፡ ዘይወድቅ ፡ ዲበ ፡ ፩ዱ ፡ ወይመውት ፡ ከመ ፡ ዘትድኅፅ ፡ እግሩ ፡ ወይወድቅ ፡ ላዕለ ፡ ዕንሰት ፡ ወይቀትላ ፡ አው ፡ ለዘበንዋሙ ፡ ይለክብ ፡ ዲበ ፡ ሕፃን ፡ በኢያእምሮ ፡ ወይቀትሎ ፡ እንዘ ፡ ይትመየየጥ ፡ አው ፡ ዘይትዐቀፍ ፡ በእብን ፡ ወይወድቅ ፡ ውእቱ ፡ እብን ፡ እመካን ፡ ልዑል ፡ ላዕለ ፡ ፩ዱ ፡ ብእሲ ፡ ወይቀትሎ ፡ ወለእሉሰ ፡ ኢይረክቦሙ ፡ ዕዳ ፡ ወዘንተኒ ፡ ሥጋዊ ፡ ወለእመ ፡ ይለወ ፡ ይዕርቅዎሙ ፡ አው፡



ግሯል ። ይኸውም ፡ በ፴፰ኛውና ፡ ወደዚህ ፡ በሚያመለክተው ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ ነው ።

፩ሺ፮፻፹፱ ሁለተኛው ፡ የአገዳደሉ ፡ አኳኋን ፡ ባይታወቅ ፡ እንስሳን ፡ እንደሚመታ ፡ ያላየውን ፡ ሰው ፡ ቢመታ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ዱር ፡ የወረወረ፡ ወይም ፡ በመውደቁ ፡ ያላሰበውን ፡ ግድግዳ ፡ የሚጥል ፡ ወይም ፡ ባሪያና ፡ የሚያጠፉ ፡ እንስሳዎች ፡ ባይኖሩት ፡ ወይም ፡ በጕዳና ፡ ጉድጓድና፡ የፈረሰ ፡ ሰገነት ፡ ባይኖረው ፡ ለተማችና ፡ ለወርዋሪ ፡ ቅጣታቸው ፡ ስደት ፡ ይሁን ። ባሪያውንና ፡ እንስሶቹን ፡ ግን ፡ በአለደሙ ፡ ይውሰዳቸው ። ባለሰገነቱን ፡ ወይም ፡ ባለጉድጓዱን ፡ ወይም ፡ ባለ ፡ ግንቡን ፡ ዕዳ ፡ ምንም ፡ አያገኛቸውም ።

፩ሺ፮፻፺ ፲ኛ ፡ ክፍል ። ሰውን ፡ አስሮ ፡ ወደሚሻው ፡ መድረሱን ፡ የሚከለክለው ፡ እንዲሞትም ፡ ሌሎች ፡ ወደእርሱ ፡ እንዳይደርሱ ፡ የከለከለ ፡ በረኃብም ፡ ቢሞት ፡ ወይም ፡ ዐውቆ ፡ ከሚገድል ፡ ጋር ፡ ቢያሳድረውና ፡ ቢገድለው ፡ ይኸውም ፡ እንደ ፡ አንበሳና ፡ እንደእባብ ፡ ያለ ፡ ነው ። የዚህም ፡ ፍርዱ ፡ ዐውቆ ፡ እንደገደለ ፡ ሰው ፡ ፍርድ ፡ ነው ።

፩ሺ፮፻፺፩ ፲፩ኛ ፡ ክፍል ። በሞት ፡ ምክንያት ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ምስክር ፡ የሚሆን ፡ ሁሉ ፡ ቢገድሉት ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሐሰት ፡ እንደመሰከረበት ፡ ቢታወቅ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ይገደል ። በኦሪትና ፡ በመጻሕፍት ፡ እንደተነገረ ። ይህም ፡ አስቀድሞ ፡ በአንቀጸ ፡ ሰማዕት ፡ ተነግሯል ። (ፍ ፡ ነ ፡ ፩ሺ፭፻፲፭ - ፩ሺ፭፻፲፯) ። ዳኛ ፡ በሞት ፡ ፈርዶ ፡ ሰው ፡ ቢገደል ፡ ከዚህ ፡ በኋላ በሟች ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ ይህን ፡ በመሰለው ፡ ላይ ፡ የምስክሮችን ፡ ሐሰት ፡ እያወቀ ፡ በዓመፅ ፡ እንደፈረደ ፡ ቢታወቅ ፡ የሚሆነው ፡ ሁሉ ፡ ይጨመራል ።

፩ሺ፮፻፺፪ ፲፪ኛ ፡ ክፍል ። አንዱ ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ ቢወድቅበትና ፡ ቢሞት ፡ ይሙት ፡ ቢቃ ፡ እንዳይፈርዱ ፡ ይናገራል ። ይኸውም ፡ እግሩ ፡ እድጦት ፡ በጸነሰች ፡ ሴት ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ እንደሚገድላት፡ ወይም ፡ በእንቅልፉ ፡ ሲገለባበጥ ፡ ባለማወቅ ፡ በሕፃኑ ፡ ላይ ፡ ተኝቶ ፡ እንደሚገድለው ፡ ወይም ፡ በደንጋይ ፡ ተሰናክሎ ፡ ያ ፡ ድንጋይ ፡ ከከፍታ ፡ ቦታ ፡ በአንድ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ እንደሚገድለው ፡ ያለ ፡ ነው ። እሊህንስ ፡ ዕዳና ፡ ሥጋዊ ፡ ቅጣት ፡ አያገኛቸውም ። ቢመ

ይስድድዎሙ ።

፩ሺ፮፻፶፫ ወበዝንቱ ፡ እንቀጽ ፡ ሀሎ ፡ ቦቱ ፡ ካልእ ፡ ተጋእዞ ፡ ዘኢዘከርነ ፡ ወይወፅእ ፡ ፍትሕ ፡ ዚእሁ ፡ እምዘ ፡ ዘክርነ ፡ ሶበ ፡ ተደመረ ፡ ተመክንዮ ፡ ዘቀዳሚ ፡ ምስለ ፡ ካልእ ፡ ተመክንዮ ፡ ሶበ ፡ ይትጋፋእ ፡ ብእሲ ፡ ምስለ ፡ ብእሲ ፡ በመካነ ፡ ልዑል ፡ ወያወድቆ ፡ ወይቀትሎ ፡ ካልእ ፡ በሰይፍ ፡ እው ፡ ዘይመስሎ ፡ ለዝንቱ ፡ በዘይመውት ፡ እው ፡ ዘይወድቅ ፡ እንዘ ፡ ሕያው ፡ ወይወግእ ፡ ላሕም ፡ ወይመውት ፡ ሶቤሃ ። ወዓዲ ፡ ከመ ፡ ዘይወግሮ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡ ለዘየእምር ፡ ጸቢተ ፡ ወይውኅጦ ፡ እንበሪ ፡ ወከመ ፡ ዘያቈስሎ ፡ ብእሲ ፡ ለብእሲ ፡ ወይደዊ ፡ ወያቈስሎ ፡ ካልእ ፡ ዳግመ ፡ ወይመውት ፡ በደዌሁ ፡ ዳግማዊ ፡ ለእሉ ፡ ምግባራት ፡ ወዘይመስሎሙ ፡ ይሕትቱ ፡ መፍቅደ ፡ ዚእሁ ፡ ለገባሪ ።

፩ሺ፮፻፶፬ ወለእመ ፡ ኀብሩ ፡ ብዙኃን ፡ በብእ ፡ ለቀቲለ ፡ ፩ዱ ፡ ወተሳተፉ ፡ በእንተ ፡ ቀቲሎቱ ፡ በገቢር ፡ በተኃብሮት ፡ ይትቀተሉ ፡ ቦቱ ።

፩ሺ፮፻፶፭ ወለእመ ፡ ቀተለ ፡ ፩ዱ ፡ ብእሲ ፡ ብዙኃን ፡ ሰብእ ፡ ወኢተቀትለ ፡ ዘእንበሌሁ ፡ ወፍትሕ ፡ ላዕለ ፡ ግብር ፡ እንተ ፡ ወድቀ ፡ ውስቴታ ፡ ቀትል ፡ እኮ ፡ ላዕለ ፡ ዘይትሔደስ ፡ እምድኅሬሃ ፡ ከመ ፡ ዘይቀትል ፡ ወውእቱ ፡ እንዘ ፡ ንኡስ ፡ አው ፡ ስቡድ ፡ ወኢይትኃሠሥ ፡ እምኔሁ ፡ ፍትሐ ፡ ተማሣጽ ፡ ጊዜ ፡ ልህቀቱ ፡ አው ፡ ድኅረ ፡ ተእትቶተ ፡ ዕበዱ ።

፩ሺ፮፻፶፮ ወኢይከውን ፡ ዕርቁ ፡ ዘቤዛ ፡ ወኢ ፡ በተሰዶ ፡ ዘየንተ ፡ ንስሐ ፡ ዳእሙ ፡ ይትኀደግ ፡ በንስሓ ፡ እስመ ፡ ንስሓ ፡ ተማሣጽ ፡ ነፍሳዊ ፡ ቤዛሰ ፡ ወተሰዶ ፡ ተማሣጽ ፡ ሥጋዊ ፡ ወቀትል ፡ ዘይከውን ፡ እምብእሲ ፡ በእእምሮ ፡ እኮ ፡ ውእቱ ፡ ነፍስ ፡ ባሕቲቱ ፡ ወኢ ፡ ሥጋ ፡ ባሕቲቱ ።

፩ሺ፮፻፶፯ ወእእምር ፡ ከመ ፡ ሥምረተ ፡ ዝንቱ ፡ እንቀጽ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ዘፈቀደ ፡ ቀቲለ ፡ ብእሲ ፡ ወቀተሎ ፡ ፍትሑኬ ፡ ከመ ፡ ይትቀተል ፡ እው ፡ በከመ ፡ ሥምሩ ፡ ሰብእ ፡ ቅቱል ፡ እመኒ ፡ ፈድየ ፡ ሰዳ ፡ አው ፡ ከመ ፡ ይሥረዩ ፡ ሎቱ ፡ በኵሉ ፡ ወለእመ ፡ ኢቀተለ ፡ በፈቃዱ ፡ ይስደድ ።

፩ሺ፮፻፶፰ መክ ፡ ፵ወ፱ቱ ፡ ፹ወ፯ቱ ፡ ወዘቀተለ ፡



ችም ፡ ያስታርቋቸው ፡ ወይም ፡ ይስደዱዋቸው ።

፩ሺ፮፻፶፫ በዚህ ፡ እንቀጽ ፡ ያልተናገርነው ፡ ሌላ ፡ ክርክር ፡ አለ ። የቀደመው ፡ ምክንያት ፡ ከሌላው ፡ ምክንያት ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ቢሆንም ፡ ከተናገርነው ፡ ፍርዱ ፡ ይወጣል ። ከፍ ፡ ባለ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ሰው ፡ ከሰው ፡ ጋራ ፡ ቢጋፋ ፡ ቢጥለውም ፡ ሌላም ፡ ሰው ፡ (ከታች ፡ ያለ) ፡ በሰይፍ ፡ ቢገድለው ፡ ወይም ፡ በሚሞት ፡ ሁናቴ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ደኅና ፡ ሳለ ፡ የወደቀ ፡ በሬም ፡ ቢወጋውና ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ቢሞት ፡ ዳግመኛም ፡ ዋና ፡ የሚያውቀውን ፡ ሰው ፡ ከባሕር ፡ ቢጥለውና ፡ ዐንበሪ ፡ ቢውጠው ፡ እንዱም ፡ እንዱን ፡ ቢያቆስለውና ፡ ቢታመም ፡ ዳግመኛም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ቢያቆስለውና ፡ በሁለተኛው ፡ ቁስል ፡ ቢሞት ፡ እኒህን ፡ ሥራዎችንና ፡ የመሰሉትን ፡ የሠራውን ፡ ሰው ፡ ፈቃድ ፡ ይመርምሩ ።

፩ሺ፮፻፶፬ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ እንድ ፡ ሰው ፡ ለመግደል ፡ ቢተባበሩ ፡ እርሱንም ፡ ስለመግደል ፡ በሥራ ፡ በመተባበር ፡ እንድ ፡ ቢሆኑ ፡ በእርሱ ፡ ይገደሉ ።

፩ሺ፮፻፶፭ አንድ ፡ ሰው ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ቢገድል ፡ ያለእርሱ ፡ ሌላ ፡ አይሙት ። አገዳደል ፡ በሆነባት ፡ ሥራ ፡ ፍርድ ፡ አለ ። ከእርሱዋም ፡ በኋላ ፡ እንደገዳይ ፡ የሚታደስ ፡ አይደለም ። ይኸውም ፡ ሕፃን ፡ ወይም ፡ ዕብድ ፡ ሳለ ፡ ነው ። ባደገ ፡ ጊዜና ፡ ዕብደቱ ፡ ከተወው ፡ በኋላ ፡ የቅጣት ፡ ፍርድ ፡ ከእርሱ ፡ አይፈላለጉ ።

፩ሺ፮፻፶፮ ዕርቁም ፡ በንስሐ ፡ ፈንታ ፡ በካሳና ፡ በስደት ፡ አይሁን ። በንስሐ ፡ ይቅር ፡ እንጂ ። ንስሐ ፡ መንፈሳዊ ፡ ቅጣት ፡ ነውና ። ካሣና ፡ ስደት ፡ ግን ፡ ሥጋዊ ፡ ቅጣት ፡ ነው ። በዕውቀት ፡ ከሰው ፡ የሚሆን ፡ አገዳደል ፡ ነፍስ ፡ ብቻ ፡ ወይም ፡ ሥጋ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።

፩ሺ፮፻፶፯ የዚህ ፡ አንቀጽ ፡ አስተያየቱ ፡ ሰውን ፡ መግደልን ፡ ወዶ ፡ በገደለ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ እንዲሆን ፡ እወቅ ። ፍርዱም ፡ እንዲገደል ፡ ወይም ፡ የሟች ፡ ሰዎች ፡ የደም ፡ ዋጋ ፡ ለማስከፈልም ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ፈጽመው ፡ ይቅር ፡ ይሉት ፡ ዘንድም ፡ ቢሆን ፡ እንደ ፡ ወደዱ ፡ ነው ። በፈቃዱ ፡ ባይገድል ፡ ግን ፡ ይሰደድ ።

፩ሺ፮፻፶፰ መክ ፡ ፵፱ ። ፹፯ ። ሳያውቅ ፡ መግደልን ፡

ቀቲሉ ፡ እንበለ ፡ አእምሮቱ ፡ ይሰደድ ።

፩ሺ.፯፻ ፺፱ ትዳ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘዘበጠ ፡ ኪያሁ ፡ ግብተ ፡ ዘእንበለ ፡ ተዓርሮት ፡ እው ፡ ወገሮ ፡ በእብን ፡ ዘእንበለ ፡ እከዩ ፡ እው ፡ በካልኡ ፡ ለውእቱ ፡ እምዘይቀትል ፡ እንበለ ፡ ያእምር ፡ ከመ ፡ ይመውት ፡ ወሞተ ፡ ውእቱ ፡ ወኢኮነ ፡ ፀሩ ፡ እንዘ ፡ ኢይፈቅድ ፡ አእከዮቶ ፡ ይፍትሑ ፡ ማእከሌሁ ፡ ወማእከለ ፡ ኅማሚ ፡ ደም ፡ ወይርአዩ ፡ ዘንተ ፡ ወያድኅንዎ ፡ እም እደ ፡ ኅማሜ ፡ ደም ፡ ወይትፈነው ፡ ውስተ ፡ ሀገር ፡ ወይንበር ።

፩ሺ.፯፻ ትቤ ፡ ወለእመ ፡ ኢፈቀደ ፡ ቀቲሎቶ ፡ ወባሕቱ፡ እግዚአብሔር ፡ ረሰየ ፡ ቦቱ ፡ ቀትለ ፡ ላዕለ ፡ እዴሁ ፡ ይትመኀፀን ፡ ኀበ ፡ መካን ፡ ዘእግዚአ ብሔር ፡ እመሰ ፡ ረከቦ ፡ በዓለ ፡ ደም ፡ በአፍኣ ፡ ወቀተሎ ፡ አልቦቱ ፡ ዕዳ ።

፩ሺ.፯፻፩ መካ ፡ ፴፩ ፡ ወዘየዐይይ ፡ ዘተማኅፀነ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅድስት ፡ በመባሕተ ፡ ርእሱ ፡ ወያወፅእ ፡ እምኔሃ ፡ ይዘብጥዎ ፡ ወይ ላጽዩ ፡ ሥዕርቶ ፡ ወይሰድድዎ ፡ ወይንበር ፡ ለዓለም ፡ በስደት ። ወእመሰ ፡ ኢክህለ ፡ ከመ ፡ ይጕየይ ፡ መካ ፡ ፻ወ፩ ፡ ይፍትሑ ፡ ፈታሕት ፡ ማእከለ ፡ ቀታሊ ፡ ወማእከለ ፡ ሰብእ ፡ ደም ፡ በሰርቅ ፡ ወያድኅንዎ ፡ እምኔሆሙ ፡ እመኒ ፡ ፈቀዱ ፡ ወእበዩ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ኢፈቀደ ፡ ቀቲሎቶ ።

፩ሺ.፯፻፪ ወለእመ ፡ ውእቱ ፡ ተዓበየ ፡ ወአስተርአየ ፡ ላዕለ ፡ ሰብአ ፡ ቅትል ፡ ወተመክሐ ፡ ላዕሌ ሆሙ ፡ ሶበ ፡ ቀተልዎ ፡ አልቦ ፡ ዕዳ ፡ ላዕሌ ሆሙ ፡ ወኢነሥኡ ፡ ለቀታሊያኒሁ ፡ እስመ ፡ ኮነ ፡ ዘዩደሉ ፡ ላዕሌሁ ፡ ከመ ፡ ኢያስተርኢ ፡ እስከ ፡ ይትፈጸም ፡ መዋዕለ ፡ ኅዘኖሙ ።

፩ሺ.፯፻፫ ክፍል ፡ ዘዩፈትሕ ፡ በእንተ ፡ ቀትል ፡ ዘው ዑእ ፡ እምዘተነግረ ፡ ቅድመ ፡ ወዘያንብር ፡ ፪ተ ፡ አናቅጸ ፡ ፍሉጣነ ። ወሶበ ፡ ተበአሱ ፡ ፪ቱ ፡ እደው ፡ ወዘበጡ ፡ ብእሲተ ፡ ፅንስተ ፡ ወእው ፅአ ፡ እጓለ ፡ እምከርሣ ፡ ወእመ ፡ መንፈስ ፡ ኢይትዌለድ ፡ ላዕለ ፡ ዓዕዓዕ ፡ ዓዲሁ ፡ ይፍዲ ፡ ዘተፍታ ፡ ለብእሲት ፡ እምጣነ ፡ አያሮ ፡ ምታ ፡ በፍትሕ ፡ ፈታሒ ። እመሰ ፡ መንፈስ ፡ ሀለወ ፡



የገደለ ፡ ይሰደድ ።

፩ሺ.፯፻ ፺፱ ትዳ ። ያለ ፡ ጠብ ፡ በድንገት ፡ የመታው ፡ ቢሆን ፡ ወይም ፡ ያለተንኰል ፡ በደንጋይ ፡ ወይ ም ፡ ከሚገድል ፡ ወገን ፡ ከዚህ ፡ በሌላ ፡ እንደ ሚሞት ፡ ሳያውቅ ፡ ቢመታውና ፡ ያ ፡ ሰው ፡ ቢሞት ፡ ክፉ ፡ ሊያደርግበት ፡ ሳይወድ ፡ ጠላቱ፡ ካልሆነ ፡ በእርሱና ፡ በደም ፡ ፈላጊ ፡ መካከል ፡ ይፍረዱ ። ይህንም ፡ መርምረው ፡ ከደም ፡ ፈላ ጊው ፡ እጅ ፡ ያድኑት ። ወደሌላም ፡ ሀገር ፡ ተሰ ድዶ ፡ ይኑር ። (ዘኍ ፡ ፴፭ ፡ ፳፪ - ፳፯) ።

፩ሺ.፯፻ ትቤ ። ሊገድለው ፡ ባይወድ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እግዚ አብሔር ፡ ሞቱን ፡ በእጁ ፡ ቢያደርግበት ፡ በቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይማፀን ። ነገር ፡ ግን ፡ ባለደሙ ፡ በአፍኣ ፡ አግኝቶ ፡ ቢገድለው ፡ ዕዳ ፡ የለበትም ። (ዘፀ ፡ ፳፩ ፡ ፲፪ - ፲፫) ።

፩ሺ.፯፻፩ መካ ፡ ፴፱ ። በቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተማፀነውን ፡ በራሱ ፡ ሥልጣን ፡ ቀምቶ ፡ ከእ ርሱዋ ፡ ቢያወጣው ፡ ይግረፉት ። ፀጕሩን ፡ ላጭ ተዉም ፡ ይስደዱት ። ለዘለዓለምም ፡ በስደት ፡ ይኑር ። ሊሸሽ ፡ ባይችል ፡ ግን ፡ መካ ፡ ፻፩ ። ዳኞች ፡ በገዳይና ፡ በባለደሞች ፡ መካከል ፡ በስ ርቅ ፡ ፈርደው ፡ ከእነርሱ ፡ ያድኑት ። ቢወዱም፡ እንቢ ፡ ቢሉም ። እርሱ ፡ ሊገድለው ፡ አልወደ ደምና ።

፩ሺ.፯፻፪ እርሱ ፡ በሟች ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ ኰርቶ ፡ ቢታይ፡ ቢመካባቸውና ፡ ቢገድሉትም ፡ ዕዳ ፡ የለባቸ ውም ። ለገዳዮችም ፡ ቅጣት ፡ የለባቸውም ። ለእርሱ ፡ የሚገባው ፡ መዋዕለ ፡ ኀዘናቸው ፡ እስ ኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ እንዳይታይ ፡ መሆን ፡ ነበ ረና ።

፩ሺ.፯፻፫ ክፍል ። አስቀድሞ ፡ ከተነገረው ፡ የተለየ ፡ ስለ እንዳይል ፡ የሚፈርድ ፡ ልዩ ፡ የሆኑ ፡ ሁለት ፡ አንቀጾችንም ፡ የሚያኖር ፡ ነው ። ሁለት ፡ ወን ዶች ፡ ተጣልተው ፡ ያረገዘች ፡ ሴትን ፡ ቢመ ቱና ፡ ፅንሱን ፡ ከሆዷ ፡ ቢያስወጡ ፡ በጭንጋ ፉም ፡ ላይ ፡ ገና ፡ ነፍስ ፡ ባይንቀሳቀስ ፡ ሴቲ ቱን ፡ ገፍቶ ፡ የጣላት ፡ ሰው ፡ ባሏ ፡ በዳኛ ፡ ፍርድ ፡ ያስፈረደበትን ፡ ያህል ፡ ይክፈል ። በጭ ንጋፉ ፡ ላይ ፡ ነፍስ ፡ ቢኖር ፡ ግን ፡ የነፍስ ፡

ላዕለ ፡ ዓዕዓዕ ፡ ነፍስ ፡ በዘ ፡ ነፍስ ፡ መክ ፡ ፻፸፩ ፡ እንበለ ፡ ዘተጸገወ ፡ ወተማረዩ ።

፩ሺ፯፻፬ መክ ፡ ፴፴፩ ፡ ወእግብርትኒ ፡ እለ ፡ ይፈቅዱ ፡ አጥፍኦተ ፡ ሕይወተ ፡ እጋእዝቲሆሙ ፡ ይትወደዩ ፡ ውስተ ፡ እሳት ። ወይትኩነኑ ፡ ካዕበ ፡ እግብርት ፡ እለ ፡ ሰምዑ ፡ ጽራኀ ፡ እግዚእሙ ፡ ወሙእቱ ፡ እንዘ ፡ ይትቀተል ፡ እው ፡ እእመሩ ፡ እው ፡ ጠየቁ ፡ በዘኮነ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወኢረድእዎ ፡ እመኒ ፡ ኮነ ፡ ዝንቱ ፡ ውስተ ፡ ዓፀድ ፡ እው ፡ ውስተ ፡ ሐቅል ፡ እው ፡ ውስተ ፡ ፍኖት ።

፩ሺ፯፻፭ ወእመ ፡ አስተዋደዩ ፡ ገብር ፡ በሕይወተ ፡ እግዚኡ ፡ ይትቀተል ፡ ለእመ ፡ ኢኮነ ፡ አስተዋድዮቱ ፡ ዘይሜኒ ፡ ለሕይወተ ፡ ንጉሥ ። ወከማሁ ፡ እግዓዝያንኒ ፡ ሶበ ፡ አምጽኡ ፡ አበሳ ፡ ላዕለ ፡ ሕይወተ ፡ እጋእዝቲሆሙ ፡ ወዘይሠምር ፡ ለእከዮ ፡ ሕይወተ ፡ ንጉሥ ፡ ይትቀተል ፡ ወይትሀየድ ፡ ንዋዮ ።

፩ሺ፯፻፮ ወዓዲ ፡ ይትቀተል ፡ ዘየዐቅብ ፡ ቀታልያነ ፡ ምእመናን ፡ ወዘይረውዕ ፡ ለእርድኦተ ፡ ጸላእቶሙ ፡ ወይነግሮ ፡ ግብራቲሆሙ ፡ ወምሥጢራቲሆሙ ፡ ወዘይትጌበር ፡ ሎሙ ፡ ግብራተ ፡ ጸብእ ፡ ዘከመ ፡ አሕማር ፡ ወዘይሠይጥ ፡ ሎሙ ፡ ንዋየ ፡ ሐቅል ፡ ወዘይመስሎ ፡ ያብእዎሙ ፡ በመካን ፡ ዘአበሉ ፡ ቦቱ ፡ ከመ ፡ ይትገሥጹ ፡ ባዕዳን ፡ በእሉ ፡ እለ ፡ ይፈቅዱ ፡ ከዊነ ፡ ኀበ ፡ ዝንቱ ፡ ግብር ፡ ወይኩን ፡ ትፍሥሕት ፡ ለሰብእ ፡ ቅቱላን ።

፩ሺ፯፻፯ ክፍል ፡ በእንተ ፡ ፍጻሜ ፡ አንቀጽ ፡ ዘተማጽ ፡ ሥጋዊ ። ትሔ ፡ ይከውኖ ፡ ለአበ ፡ ደም ፡ ከመ ፡ ይቅትሎ ፡ ቀታሊ ፡ ወኢይቅትሎ ፡ በመባሕተ ፡ ርእሱ ፡ ዘእንበለ ፡ ያቅሞ ፡ ቅድመ ፡ ፈታሒ ።

፩ሺ፯፻፰ ወዘቀተለ ፡ ነፍሰ ፡ ይትቀተል ፡ በስምዐ ፡ ፪ቱ ፡ ሰማዕታት ፡ ወኢይደሉ ፡ ቀቲሎተ ፡ ነፍስ ፡ በ፩ዱ ፡ ሰማዕት ፡ ወኢትንሣእ ፡ ሕልያነ ፡ በዝንቱ ።

፩ሺ፯፻፱ መክ ፡ ዘ፻ወ፳፱ቱ ፡ ኢይደልዎ ፡ ለአበ ፡ ደም ፡ ከመ ፡ ይቅትሎ ፡ ለጸላኢሁ ፡ በእደዊሁ ፡ እላ ፡ ያብጽሖ ፡ ኀበ ፡ መኰንን ፡ ከመ ፡ ይቅትሎ ። ዘ፻ወ፴ቱ ፡ ወኢይደሉ ፡ ዝንቱ ፡ ለ፩፩ሂ ፡ እላ ፡ ያብጽሖ ፡ ኀበ ፡ መኰንን ፡ ከመ ፡ ይኩንኖ ፡



ዋጋ ፡ ነፍስ ፡ ነው ። መክ ፡ ፻፩ ። ገንዘብ ፡ የተቀበሉና ፡ ይቅር ፡ የተባባሉ ፡ ቢሆኑ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፩ሺ፯፻፬ መክ ፡ ፴፱ ። የጌታቸውን ፡ ሕይወት ፡ ሊያጠፉ ፡ የሚወዱ ፡ ባሮችም ፡ ወደ ፡ እሳት ፡ ይጣሉ ። ዳግመኛም ፡ የጌታቸውን ፡ ጩኸት ፡ የሰሙ ፡ ባሮች ፡ ይኸውም ፡ ሲገደል ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ የሆነውን ፡ አውቀው ፡ ወይም ፡ ተረድተው ፡ ባይረዱት ፡ ይቀጡ ። ይህ ፡ በሰፈር ፡ ወይም ፡ በበረሃ ፡ ወይም ፡ በመንገድ ፡ ቢሆን ።

፩ሺ፯፻፭ ነገር ፡ ሥራዉ ፡ ለንጉሥ ፡ ሕይወት ፡ የሚበጅ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ባሪያ ፡ በጌታው ፡ ሕይወት ፡ ነገር ፡ ቢሠራ ፡ በሞት ፡ ይገደል ። እንደዚሁም ፡ ጨዋዎች ፡ በጌቶቻቸው ፡ ሕይወት ፡ ላይ ፡ ጉዳት ፡ ቢያመጡ ፡ የንጉሥን ፡ ሕይወት ፡ ለማጥፋትም ፡ የሚወድ ፡ ይገደል ። ገንዘቡንም ፡ ይቀማ ፡ (ይወረስ) ።

፩ሺ፯፻፮ ዳግመኛም ፡ የምእመናንን ፡ ገዳዮች ፡ የሚጠባበቅ ፡ ጠላቶቻቸውንም ፡ ለመርዳት ፡ የሚፋጠን ፡ ይገደል ። ሥራቸውንና ፡ ምሥጢራቸውንም ፡ የሚናገር ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ የሚሠራላቸው ፡ ይኸውም ፡ እንደመርከብ ፡ ያለ ፡ ነው ። የጦር ፡ መሣሪያ ፡ የመሰለውንም ፡ የሚሸጥላቸውም ፡ በሠሩት ፡ ሥራ ፡ ይቅጡአቸው ። በዚህም ፡ ሥራ ፡ መኖርን ፡ የሚፈቅዱ ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ በእሊህ ፡ ይቀጡ ፡ ዘንድ ፡ ደስታም ፡ ለሟች ፡ ወገኖች ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ።

፩ሺ፯፻፯ ክፍል ። ስለ ፡ ሥጋዊ ፡ ቅጣት ፡ አንቀጽ ፡ መጨረሻ ፡ ይናገራል ። ትሄ ። ባለደም ፡ ገዳይን ፡ ሊገድል ፡ ይገባዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ ከዳኛ ፡ ፊት ፡ ሳያደርስ ፡ አይግደለው ። (ዘዳ ፡ ፲፱ ፡ ፲፪ -፲፫) ።

፩ሺ፯፻፰ ነፍስ ፡ የገደለ ፡ ሰው ፡ በ፪ ፡ ምስክር ፡ ይገደል ። በአንድ ፡ ምስክር ፡ ነፍስ ፡ መግደል ፡ አይገባም ። በዚህም ፡ መማለጃ ፡ አትቀበል ። (ዘዳ ፡ ፲፯ ፡ ፮ - ፰) ።

፩ሺ፯፻፱ መክ ፡ ፻፳ ። ለበዓለደም ፡ ጠላቱን ፡ በእጁ ፡ ሊገድል ፡ አይገባውም ። ይገድለው ፡ ዘንድ ፡ ከዳኛ ፡ ያድርሰው ፡ እንጂ ። ፻፴ ። ይህ ፡ ለአንድ ፡ ሰው ፡ እንኳን ፡ አይገባም ። እንደ ፡ ኃጢአቱ ፡ ይፈርድበት ፡ ዘንድ ፡ ከዳኛ ፡ ያድርሰው ፡ እንጂ ።

በከመ ፡ እበሳሁ ።

፩ሺ፯፻፲ ትሔ ፡ ፳፡ ፡ መክ ፡ ፲ወ፩፡ ፡ ወኢይደሉ ፡ ለአበ ፡ ደም ፡ ከመ ፡ የሀብ ፡ ቤዛ ፡ ቅቱል ፡ ወይ ሰንአው ፡ ቦቱ ፡ ወለበዓለ ፡ ዕዳሁሰ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይንሣእ ፡ ቤዛ ፡ ወፍትሐ ፡ ዘተነጸሬ ።

በሐሰት ፡ ከመ ፡ ይትገአዞ ፡ ክሡተ ፡ ወመጠዎ ፡ ለሰይፍ ፡ ወእሳት ፡ ወከማሁ ፡ ይግበሩ ፡ ቦቱ ፡ በከመ ፡ ገብረ ፡ ላዕለ ፡ ቢጹ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ፈቀደ ፡ ቀቲሎቶ ። እስመ ፡ ውእቱ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስተ ፡ ኦሪት ፡ ዘይብል ፡ ኵሉ ፡ ዘከዐወ ፡ ደመ ፡ ሰብእ ፡ ህየንተ ፡ ደመ ፡ ገብኡ ፡ ይትከዐው ፡ ደሙ ። ጠስ ፡ ፹ወ፱ቱ ፡ ወለመስተዋድያኒ ፡ ይደልዎ ፡ ገንቱ ፡ ዘተነአ ፡ በጊዜሁ ፡ በከመ ፡ አስተዋደዮ ፡ ለገዙ ።

፩ሺ፯፻፲፪ ትሔ ፡ ፳፡ ፡ መጅ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ወእምከመ ፡ ረከብክሙ ፡ ቅቱለ ፡ ዘግዱፍ ፡ ውስተ ፡ በድው ፡ አው ፡ ውስተ ፡ ገራህት ፡ ወኢተበውቀ ፡ ቀታ ሊሁ ፡ አሚሃ ፡ ይፃኡ ፡ መኳንንቲክሙ ፡ ወእእ ሩጊክሙ ፡ ወይስፍሩ ፡ ማእከለ ፡ መካነ ፡ ቅቱል ፡ ወሀገር ፡ ወእደኒ ፡ ሀገር ፡ ዘኮነት ፡ ቅር ብተ ፡ ኅበ ፡ ቅቱል ፡ እሚሃ ፡ ይምሐሉ ፡ እእ ሩግ ፡ ይእቲ ፡ ሀገር ፡ ወይበሉ ፡ ኢከዐዋ ፡ እደ ዊነ ፡ ዘንተ ፡ ደመ ፡ ወኢርኢነ ፡ ዘቀተሎ ፡ ወእ ንትሙሂ ፡ ሕትቱ ፡ በእንተ ፡ ደም ፡ ወፍትሑ ፡ በጽድቅ ።

ጠብ ፡ ፵ወ፯ቱ ፡ ካህን ፡ እመ ፡ ተቃተለ ፡ ምስለ ፡ ፩ዱሂ ፡ ወይበጽሖ ፡ እስከ ፡ ይመውት ፡ ይትመ ተር ፡ በእንተ ፡ ጽንዐ ፡ ልቡ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ሕዝባዌ ፡ ይሰደድ ።

፩ሺ፯፻፲፬ ዕንቆራ ፡ ፳ወ፩ዱ ፡ ወዘይቀትል ፡ በፈቃዱ ፡ ይደልዎ ፡ ንስሓ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ሕይወቱ ፡ ወአመ ፡ ፍጻሜ ፡ ሕይወቱ ፡ ይትዐወቅ ፡ ፍጻሜ ፡ ተሳትፎቱ ፡ ምእመናን ፡ በቍርባን ።

፩ሺ፯፻፲፭ ዘ፳ወ፪ቱ ፡ ወዘሰ ፡ ቀተለ ፡ ዘእንበለ ፡ ፈቃዱ ፡ ትእዛዝ ፡ ቀዳማዊ ፡ ከመ ፡ ይትመጠው ፡ ንስሓ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ፯ቱ ፡ ዓመት ፡ በመዓርግ ትሑት ፡ ወዳግምኒ ፡ ይኩን ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ፲ቱ ፡ ዓመት ።

፩ሺ፯፻፲፮ በሰ ፡ ዘሰ ፡ ቀተለ ፡ ብእሲተ ፡ እዘዙ ፡ ማኅበር ፡ ከመ ፡ ይሰደድ ፡ እምኀብኤ ፡ ፳ ፡ ዓመት ፡ ወይ



፩ሺ፯፻፲ ትሄ ፡ ፳ ። መክ ፡ ፲፩ ። ገዳይ ፡ የሚችን ፡ ዋጋ ፡ ሊሰጥና ፡ በዚህ ፡ ሊስማማ ፡ አይገባም ። በዓለ ፡ ደሙ ፡ ግን ፡ ዋጋና ፡ የቅጣት ፡ ፍርድ ፡ ሊቀ በል ፡ ይገባዋል ። (ዘዳ ፡ ፲፱ ፡ ፲፩ - ፲፫) ።

፩ሺ፯፻፲፩ ድስቅ ፡ ፲ ። ባልንጀራውን ፡ በአደባባይ ፡ ይከ ራከረው ፡ ዘንድ ፡ በሐሰት ፡ ቢከሰው ፡ በሰይፍ ና ፡ በእሳትም ፡ ቢያስቀጣው ፡ እርሱ ፡ በባልን ጀራው ፡ ላይ ፡ እንዳደረገው ፡ በእርሱም ፡ እንደ ዚሁ ፡ ያድርጉበት ። እርሱ ፡ ሊገድለው ፡ ወድዷ ልና ። በኦሪት ፡ የሰው ፡ ደም ፡ ያፈሰሰ ፡ ስለአፈ ሰሰው ፡ ደም ፡ ፈንታ ፡ ደሙ ፡ ይፍሰስ ፡ የሚል ተጽፏልና ። ዘጉ ፡ ፴፭ ፡ ፴፫) ። ጠስ ፡ ፹፱ ። ለነገር ፡ ሠሪም ፡ በዚያ ፡ ነገር ፡ እንደሠራ ፡ በጊዜው ፡ ይህ ፡ ቅጣት ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ፯፻፲፪ ትሄ ፡ ፳ ። መጅ ፡ ፲፪ ። በምድረ ፡ በዳ ፡ ወይም በእርሻ ፡ ላይ ፡ የወደቀ ፡ ሬሳ ፡ ብታገኙ ፡ ገዳ ዩም ፡ ባይታወቅ ፡ ያንጊዜ ፡ ዳኞቻችሁና ፡ ሽማ ግሎቻችሁ ፡ ወጥተው ፡ በሬሳው ፡ ቦታና ፡ በሀ ገር ፡ መካከል ፡ ይስፈሩ ። ወደሬሳው ፡ ቅርብ ፡ የሆነች ፡ ማንኛዪቱ ፡ ሀገር ፡ ብትሆን ፡ የጊያች ፡ ሀገር ፡ ሽማግሎች ፡ ያንጊዜ ፡ ይህን ፡ ደም ፡ እጆ ቻችን ፡ አላፈሰሱም ፡ የገደለውንም ፡ አላየንም ። ብለው ፡ ይማሉ ። እናንተም ፡ ስለደሙ ፡ መርምራችሁ ፡ በእውነት ፡ ፍረዱ ። (ዘዳ ፡ ፳፩ ፡ ፩ - ፱) ።

፩ሺ፯፻፲፫ ምዕራፍ ። ስለመንፈሳዊ ፡ ቅጣት ፡ ይናገራል። ረስጠብ ፡ ፵፯ ። ካህን ፡ ከአንድ ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ ቢጣላና ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ ቢመታው ፡ ስለ ልቡናው ፡ ጭካኔ ፡ ይሻር ። ሕዝባዊም ፡ ቢሆን፡ ይለይ ።

፩ሺ፯፻፲፬ ዕንቆራ ፡ ፳፩ ። በፈቃዱ ፡ የገደለ ፡ ሰው ፡ እስከ ፡ሕይወቱ ፡ መጨረሻ ፡ ንስሓ ፡ ይገባዋል ። በሕይወቱም ፡ መጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ በቍርባን ፡ ከምእመናን ፡ ጋር ፡ ፈጽሞ ፡ አንድ ፡ መሆኑ ፡ ይታወቃል ።

፩ሺ፯፻፲፭ ፳፪ ። ያለፈቃዱ ፡ የገደለ ፡ ሰው ፡ መጀመሪ ያው ፡ ትእዛዝ ፡ እስከ ፡ ፯ ፡ ዓመት ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ በዝቅተኛ ፡ መዓርግ ፡ ሆኖ ፡ ንስሓ ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ሁለተኛውም ፡ እስከ ፡ ፲ ፡ ዓመት ፡ መጨረሻ ፡ ይሁን ።

፩ሺ፯፻፲፮ በስ ። ሴት ፡ የገደለ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ኻያ ፡ ዓመ ት ፡ ከምእመናን ፡ ይለይ ፡ ዘንድ ፡ ማኅበር ፡

ቁም ፡ አፍአ ፡ አንቀጽ ፡ እንዘ ፡ ይበኪ ፡ ወይሬኢ ፡ አብያጺሁ ፡ ምእመናን ፡ እንዘ ፡ ይበውኡ ፡ ውሣጤ ፫ተ ፡ ዓመተ ፡ ወ፯ተ ፡ ዓመተ ፡ እንዘ ፡ ውእቱ ፡ ይቀውም ፡ ምስለ ፡ ምእመናን ፡ ፲ወ፩ ፡ ዓመተ ፡ ምስለ ፡ ንኡስ ፡ ክርስቲያን ። ወሶበ ፡ ርኢክ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ነስሐ ፡ ንስሓ ፡ ዐቢየ ፡ በእንተ ፡ ዘገብሮ ፡ አታክብድ ፡ ቦቱ ፡ ኑኀ ፡ ዕድሜ ፡ ወዘሰ ፡ ቀተለ ፡ ዘእንበለ ፡ ፈቃዱ ፡ ይትከሬል ፡ ሎቱ ፡ ሙንፈቀ ፡ ዝንቱ ፡ መዋዕል ።

አዘዙ ። ፫ ፡ ዓመት ፡ እያለቀሰ ፡ ምእመናን ፡ ጓደኞቹንም ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ሲገቡ ፡ እያየ ፡ ፯ ፡ ዓመት ፡ ከምእመናን ፡ ጋር ፡ ፲፩ ፡ ዓመት ፡ ከንኡስ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋር ፡ እየቆመ ፡ ከበር ፡ በውጭ ፡ ይቆይ ። (ይቁም) ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ ኃጢአት ፡ ፍጹም ፡ ንስሓ ፡ እንደአደረገ ፡ ባየኸው ፡ ጊዜ ፡ መዋዕለ ፡ ንስሓውን ፡ አታስረዝምበት ። ያለፈቃዱ ፡ የገደለ ፡ ግን ፡ የዚህ ፡ ዘመን ፡ እኩሌታ ፡ ይቀነስለታል ።

፩ሺ፯፻፲፯ በስ ፡ ፳ወ፯ቱ ፡ ወሶበ ፡ አድኀፀ ፡ ፩ዱ ፡ ብእሲ ፡ ዕንስ ፡ አሐተ ፡ ብእሲት ፡ በሥራይ ፡ ወነበረ ፡ ምስሌሃ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይቁም ፡ በአፍአ ፡ በኵሉ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ወበተፍጻሜተ ፡ ሕይወቱ ፡ አው ፡ በምንዳቤሁ ፡ ይኩን ፡ ድልወ ፡ ለነሢአ ፡ ምሥጢራት ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ገብረ ፡ ፪ተ ፡ ኃጣውአ ፡ ዘየዐቢ ፡ ከቡዳት ፡ ዝሙተ ፡ ወቀቲለ ፡ ነፍስ ፡ ወሥራየ ።

፩ሺ፯፻፲፯ በስ ፡ ፳፯ ። አንድ ፡ ሰው ፡ የአንዲትን ፡ ሴት ፡ ፅንስ ፡ በመድኀኒት ፡ አስወርዶ ፡ ከእርሱዋ ፡ ጋር ፡ ቢኖር ፡ በዘመኑ ፡ ሁሉ ፡ በአፍአ ፡ (በውጭ) ፡ ሊቆም ፡ ይገባዋል ። በሕይወቱም ፡ መጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ በችግሩ ፡ ጊዜ ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ለመቀበል ፡ ዝግጁ ፡ ይሁን ። እጅግ ፡ ከባዶች ፡ የሆኑ ፡ ፪ ፡ ኃጢአቶችን ፡ ሠርቷልና ። ዝሙትን ፡ ነፍስ ፡ መግደልን ፡ ሥራይን ።

፩ሺ፯፻፲፰ ዕንቀረ ፡ ፳ወ፰ቱ ፡ ወአንስትኒ ፡ ሶበ ፡ ይዜምዋ ፡ ወይቀትላ ፡ ደቂቆን ፡ ወየኀብአ ፡ ተኀጕሎቶሙ ፡ አዘዙ ፡ ቅድመ ፡ በእንቲአሆን ፡ ከመ ፡ ይጻእ ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ሞቶን ፡ ዘእንበለ ፡ ተሳትፎ ። ወባሕቱ ፡ በእንተ ፡ ብዙኅ ፡ አፍቅሮቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነ ፡ ይኩን ፡ ፲ተ ፡ ዓመተ ፡ በከመ ፡ ትእዛዛት ፡ እለ ፡ ተሠርዓ ።

፩ሺ፯፻፲፰ ዕንቀረ ፡ ፳፰ ። ሴቶች ፡ ቢሰስኑ ፡ ልጆቻቸውንም ፡ ቢገድሉ ፡ ሬሳቸውንም ፡ ቢደብቁ ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ሞታቸው ፡ ድረስ ፡ ያለመገናኘት ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ አስቀድመው ፡ አዝዘዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ እኛን ፡ ስለመውደዱ ፡ ፲ ፡ ዓመት ፡ ይሁን ። እንደተጻፉት ፡ ትእዛዞች ።

## አንቀጽ ፡ ፶ወ፱ቱ ፡

በእንተ ፡ ኵነኔ ፡ ዝሙት ፡ ሥጋዊ ፡ ወመንፈሳዊ ።

፩ሺ፯፻፲፱ ምዕራፍ ፡ ቀዳማዊ ፡ በእንተ ፡ ኵነኔ ፡ ሥጋዊ ፡ ወውእቱ ፡ ፲ቱ ፡ ክፍላት ፡ ዘተጋብአ ፡ እምአብጥሊስ ፡ ዘ፶ወ፱ቱ ። ቀዳማዊ ፡ እለ ፡ ይደምሩ ፡ ደመ ፡ ምስለ ፡ ደም ፡ እመንገለ ፡ አውስቦ ፡ ውሉድ ፡ ምስለ ፡ ወላድያኒሆሙ ፡ አው ፡ አኀው ፡ ምስለ ፡ አኀቲሆሙ ፡ እሉ ፡ ኵሎሙ ፡ ይትኰነኑ ፡ በሰይፍ ። ወለእመኒ ፡ ዘመወ ፡ ምስለ ፡ ካልአን ፡ አዝማዲሁ ፡ በአምሳለ ፡ አብ ፡ ምስለ ፡ ብእሲተ ፡ ወልዱ ፡ አው ፡ ውሉድ ፡ ምስለ ፡ ብእሲተ ፡ አቡሆሙ ፡ አው ፡ ብእሲ ፡ ምስለ ፡ ወለተ ፡ ብእሲቱ ፡ አው ፡ ምስለ ፡ ወለተ ፡ ምተ ፡ ብእሲቱ ፡ አው ፡ እኁ ፡ ምስለ ፡ ብእሲተ ፡ እኁሁ ፡

## አንቀጽ ፡ ፶፱ ።

ስለ ፡ ሥጋዊና ፡ ስለ ፡ መንፈሳዊ ፡ የዝሙት ፡ ቅጣት ፡ ይናገራል ።

፩ሺ፯፻፲፱ መጀመሪያው ፡ ምዕራፍ ፡ ስለ ፡ ሥጋዊ ፡ ቅጣት ፡ ይናገራል ። ይኸውም ፡ ከአብጥሊስ ፡ ፶፱ ፡ የተሰበሰበ ፡ ፲ ፡ ክፍል ፡ ነው ። መጀመሪያው ፡ ከመጋባት ፡ ወገን ፡ ደምን ፡ ከደም ፡ ጋራ ፡ የሚቀላቅሉ ፡ አባቶች ፡ ከልጆች ፡ ጋራ ፡ ወይም ፡ ልጆች ፡ ከወላጆቻቸው ፡ ጋራ ፡ ወይም ፡ ወንድሞች ፡ ከእኅቶቻቸው ፡ ጋራ ፡ ቢሆን ፡ እሊህ ፡ ሁሉ ፡ በሰይፍ ፡ ይቀጡ ። ከሌሎች ፡ ዘመዶቹም ፡ ጋራ ፡ ቢሰስን ፡ ለምሳሌ ፡ አባት ፡ ከልጁ ፡ ሚስት ፡ ጋር ፡ ወይም ፡ ልጆች ፡ ከአባታቸው ፡ ሚስት ፡ ጋር ፡ ወይም ፡ ወንድ ፡ ከሚስቱ ፡ ልጅ ፡ ጋር ፡ ወይም ፡ ከሚስቱ ፡ ባል ፡ ሴት ፡

አንቀጽ ፡ ፵፰ ።

አው ፡ ወልደ ፡ ብእሲ ፡ ምስለ ፡ ወለተ ፡ ብእሲተ ፡ እቡሁ ፡ አው ፡ እኁወ ፡ እብ ፡ ምስለ ፡ ወለተ ፡ እኁሁ ፡ አው ፡ ወልደ ፡ እኁው ፡ ምስለ ፡ እኅተ ፡ እቡሁ ፡ አው ፡ ፩ዱ ፡ ኀበ ፡ ፪ቲ ፡ አኃት ፡ አው ፡ ወለት ፡ ምስለ ፡ እማ ፡ በእእምሮቶሙ ፡ ይዘበጡ ፡ ወይምትሩ ፡ እእናፌሆሙ ፡ ወእለኒ ፡ ዘመዋ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ኅቡረ ።

፩ሺ፯፻፹ ዘሮወ፫ቱ ፡ እለኒ ፡ ይጼመሩ ፡ በተዋስቦ ፡ እመ ፡ ኮኑ ፡ እብ ፡ ወወልድ ፡ በእም ፡ ወወለታ ፡ አው ፡ ወልደ ፡ እኁ ፡ ኀበ ፡ ብእሲተ ፡ እኁወ ፡ እቡሁ ፡ አው ፡ ፪ቱ ፡ አኃው ፡ ለእም ፡ ወወለታ ፡ አው ፡ ወልደ ፡ እኅት ፡ ብእሲተ ፡ እኁወ ፡ እሙ ፡ አው ፡ እኁወ ፡ እም ፡ ለብእሲተ ፡ ወልደ ፡ እኅቱ ፡ ይትፈለጡ ፡ ወይዝብጥዎሙ ፡ ዝብጠተ ፡ ማሕመሜ ኅቡረ ።

፩ሺ፯፻፹፩ ሥርዋጽ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ መካን ፡ ተነግረ ፡ ዘይፈደፍድ ፡ መሀሎ ፡ ኀበ ፡ መለካውያን ፡ ወእኮ ፡ በኀቤነ ፡ ዘኢተነግረ ፡ በቀኖናት ፡ ሐዋርያት ፡ ወኢ ፡ ማኅበረ ፡ ኒቅያ ፡ ዘየኀብር ፡ ኪያሁ ፡ ዘይብል ፡ ወለእመ ፡ ኮኑ ፡ ውሉደ ፡ እኁወ ፡ እብ ፡ ወውሉዶሙ ፡ አው ፡ ፪ቱ ፡ አኃው ፡ ለ፪ቲ ፡ አኃት ።

፩ሺ፯፻፹፪ ዳግም ፡ ዘ፫ወ፫ቱ ፡ እለ ፡ ያወስቡ ፡ መነኮሳይያተ ፡ ወዲያቆናውያተ ፡ ወገዳማውያተ ፡ ይምትሩ ፡ እእናፌሆሙ ፡ ኅቡረ ።

፩ሺ፯፻፹፫ ዘ፫ወ፬ቱ ፡ እለ ፡ ያውስቡ ፡ ዓርከተ ፡ ዘጥምቀት ፡ ክርስትና ፡ እመሂ ፡ ነበሩ ፡ በሕገ ፡ ሰብሳብ ፡ አው ፡ በካልእ ፡ እምዝንቱ ፡ ይምትሩ ፡ እእናፌሆሙ ፡ ወይፍልጥዎሙ ። ወእመሰ ፡ ኮነ፡ ሎሙ ፡ ቅድመ ፡ ብእሲት ፡ ወምት ፡ ይወስክዎሙ ፡ ዙነኔ ፡ ዝብጠት ።

፩ሺ፯፻፹፬ ሣልስ ፡ ዘ፫ወ፮ቱ ፡ ዘይእኅዛ ፡ ለወለት ፡ ድንግል ፡ በግብር ፡ ይምትሩ ፡ እእናፊሁ ፡ ወየሀብዋ ላቲ ፡ ሣልስተ ፡ እድ ፡ እምንዋዩ ። ዘ፫ወ፲ቱ ፡ ወዘሂ ፡ ይእኅዛ ፡ ለወለት ፡ እምቅድመ ፡ ታብጽሕ ፡ ፲ወ፫ተ ፡ ዓመተ ፡ ይምትሩ ፡ እንፎ ፡ ወየሀብዋ ፡ ላቲ ፡ መንፈቆ ፡ ለዘእጥረዮ ።

ስለ ፡ ዝሙት ፡ ቅጣት ።

ልጅ ፡ ጋር ፡ ወንድም ፡ ከወንድሙ ፡ ሚስት ፡ ጋር ፡ ወይም ፡ የወንድ ፡ ልጅ ፡ ከእንጀራ ፡ እናቱ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ጋር ፡ ወይም ፡ የአባት ፡ ወንድም ፡ ከወንድሙ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ጋር ፡ ወይም ፡ የወንድም ፡ ልጅ ፡ ከአባቱ ፡ እኅት ፡ ጋር ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከ፪ ፡ እትማማቾች ጋር ፡ ወይም ፡ ልጅቱን ፡ ከእናቷ ፡ ጋር ፡ እያወቁ ፡ ቢደርሱ ፡ ይገረፉ ። አፍንጫቸውንም ፡ ይፎንኑ ። ከእነርሱም ፡ ጋር ፡ ያመነዘሩ ፡ ሴቶችም ፡ በአንድነት ፡ ይቀጡ ።

፩ሺ፯፻፹ ፸፫ ። በዝሙት ፡ የተገናኙ ፡ ሰዎች ፡ አባትና ፡ ልጅ ፡ በእናትና ፡ በልጇዋ ፡ ቢሆኑ ፡ ወይም ፡ የወንድም ፡ ልጅ ፡ ከአባቱ ፡ ወንድም ፡ ሚስት ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡ ወንድማማቾች ፡ በእናትና ፡ በልጇዋ ፡ ወይም ፡ የእኅት ፡ ልጅ ፡ በእናቱ ፡ ወንድም ፡ ሚስት ፡ ወይም ፡ የእናት ፡ ወንድም ፡ የእኅቱን ፡ ልጅ ፡ ሚስት ፡ ቢደርስ ፡ ይለዩ ። በአንድነትም ፡ ፅኑ ፡ ግርፋት ፡ ይግረፏቸው ።

፩ሺ፯፻፹፩ ሥርዋጽ ። በሐዋርያት ፡ መጻሕፍት ፡ ከእርሱ ጋራ ፡ በሚተባበር ፡ በኒቅያ ፡ ጉባኤም ፡ ያልተነገረ ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ ያይደለ ፡ በመለካውያውያን ፡ ዘንድ ፡ ያለ ፡ የበዛ ፡ ነገር ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ተነገረ ። እንዲህ ፡ የሚል ፡ የአባት ፡ የወንድም ፡ ልጆች ፡ ልጆቻቸውም ፡ ወይም ፡ ሁለት ፡ ወንድማማቾች ፡ ለሁለት ፡ እትማማቾች ፡ ቢሆኑ ።

፩ሺ፯፻፹፪ ሁለተኛ ፡ ፳፫ ። መነኮሳይያትንና ፡ ዲያቆናውያትን ፡ ገዳም ፡ የገቡትንም ፡ ሴቶች ፡ ያገቡትን፡ ሰዎች ፡ በአንድነት ፡ አፍንጫቸውን ፡ ይፎንኗቸው ።

፩ሺ፯፻፹፫ ፳፬ ። በጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ የተዘመዱቻቸውን ፡ የሚያገቡ ፡ ሰዎች ፡ በጋብቻ ፡ ሥርዓት ፡ ወይም ፡ ከዚህ ፡ በሌላ ፡ (በዝሙት) ፡ ቢኖሩ ፡ አፍንጫቸውን ፡ ፎንነው ፡ ይለዩአቸው ። አስቀድሞ ፡ (ለወንዱ) ፡ ሚስት ፡ (ለሴቷ) ፡ ባል ፡ ቢኖራቸው ፡ የግርፋት ፡ ቅጣት ፡ ይጨምሩባቸው ።

፩ሺ፯፻፹፬ ሦስተኛ ፡ ፳፮ ። ልጃገረዷን ፡ በግድ ፡ ቢይዛት፡ አፍንጫውን ፡ ይፎንኑት ። ለእርሱዋም ፡ ከገንዘቡ ፡ ሢሶውን ፡ ይስጧት ። ፳፱ ። አስራ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ሳይሆናት ፡ አስቀድሞ ፡ ልጃገረዲቱን ፡ የያዛትን ፡ ሰው ፡ አፍንጫውን ፡ ይፎንኑት ። ከገንዘቡም ፡ እኩሌታውን ፡ ለእርሱዋ ይስጧት ።

አንቀጽ ፡ ፶፰ ።

፩ሺ፯፻፹፩ ዘኃወፀት ፡ ወዘይነሥእ ፡ ፍንርተ ፡ ካልእ ፡ ለእመ ፡ ከነ ፡ ዝንቱ ፡ በፈቃዳ ፡ ይምትሩ ፡ አእና ፊሁ ፡ ወእእናፊሃ ። ወእመሰ ፡ ገብረ ፡ በአገ ብሮ ፡ ኪያሃ ፡ የሀብዋ ፡ ላቲ ፡ ድኅረ ፡ ተኩነነ ፡ ሣልስተ ፡ እድ ፡ እምዘአጥረየ ።

፩ሺ፯፻፹፪ ራብዕ ፡ ፃወፅዱ ፡ ወእለ ፡ ይመሥጡ ፡ ወለተ ፡ ሕፅይተ ፡ አው ፡ ዘኢተሐፅየት ፡ አው ፡ መፀስ ብተ ፡ እመ ፡ ከነት ፡ እምዘመደ ፡ ክቡራን ፡ እመሂ ፡ አመተ ፡ አው ፡ አግዓዚተ ፡ ወፈድፋ ደሰ ፡ እምእለ ፡ ከና ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ፍሉ ጣተ ፡ በግዕዘን ፡ ሶበ ፡ ገብሩ ፡ ዘንተ ፡ በጽብእ ፡ ይትኮነኑ ፡ በሰይፍ ፡ ዘገብረ ፡ ዘንተ ፡ ወእለኒ ፡ ኅብሩ ፡ ምስሌሁ ፡ በምንትኒ ፡ ፆታ ፡ ወትራድ እዎ ፡ ይዘብጡ ፡ ወይትላጸዩ ፡ ሥዕርተ ፡ ርእ ሶሙ ፡ ወይምትሩ ፡ እእናፊሆሙ ፡ ወይሰደዱ ። ወእመሰ ፡ ገብሩ ፡ ዘንተ ፡ ዘእንበለ ፡ ጽብእ ፡ ትት መተር ፡ እደ ፡ መማጢ ፡ ባሕቲቱ ፡ ወእለ ፡ ተራ ድእዎ ፡ ይዘብጡ ፡ ወይትላጸዩ ፡ ሥዕርተ ፡ ርእ ሶሙ ፡ ወይሰደዱ ።

፩ሺ፯፻፹፫ ወለእመ ፡ ተኃበለ ፡ ገብር ፡ ላዕለ ፡ መማጢ ፡ እግዝእቱ ፡ ወረድአ ፡ በዝንቱ ፡ ካልእ ፡ ያውዕ ይዎሙ ፡ በእሳት ፡ ኅቡረ ። ወለእመ ፡ እእመረ ፡ ገብር ፡ ዕግተተ ፡ በእንተ ፡ ተሀይዮተ ፡ እግዝ እቱ ፡ ወኢረድአ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ያውዕይዎ ፡ በእሳት ።

፩ሺ፯፻፹፬ ኃምስ ፡ ፳ወ፩ቱ ፡ ዘተደመረ ፡ ምስለ ፡ ወለት ድንግል ፡ በፈቃዳ ፡ ወዘእንበለ ፡ ፈቃዳ ፡ እን በለ ፡ ያእምሩ ፡ ወላድያኒሃ ፡ ለእመ ፡ ከነ ፡ ያፈ ቅር ፡ አውሰቦታ ፡ ይደልዎሙ ፡ ኅርየት ፡ ለወላ ድያኒሃ ፡ ከመ ፡ ይፈጽሙ ፡ መፍትሖ ። ወለእመ፡ እበየ ፡ ፩ዱ ፡ እምወላድያኒሃ ፡ እመ ፡ ይትከ ሀሎ ፡ ለብእሲ ፡ ዘአማሰና ፡ ወከነ ፡ ባዕለ ፡ የሀብ፡ ልጥረ ፡ ወርቅ ፡ ወእመ ፡ ኢይትከሀሎ ፡ የሀብ ፡ መንፈቀ ንዋዩ ፡ እመሰ ፡ ከነ ፡ ነዳየ ፡ በኵሉ ፡ ይዝብጥዎ ፡ ወይላጽይዎ ፡ ርእሶ ፡ ወይሰድድዎ።

፩ሺ፯፻፹፭ ሳድስ ፡ በእንተ ፡ ዘትዝሙ ፡ ምስለ ፡ ገብር፡ እው ፡ ምስለ ፡ አመት ። ዘፃወ፩ቱ ፡ ብእሲት ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ምት ፡ ሶበ ፡ ዘመወት ፡ ምስለ ፡ ገብራ ፡ ይዝብጥዋ ፡ ወትትላጸይ ፡ ርእሳ ፡ ወይ ምትሩ ፡ እእናፊሃ ፡ ወይሰድድዋ ፡ እምሀገር ፡ ዘትነብር ፡ ባቲ ፡ ወትሄሉ ፡ እምትረሉ ፡ ክብሩ ፡ ወለገብርሰ ፡ ዘዘመወ ፡ ምስሌሃ ፡ ይቀንዩ ፡ ሰይፍ ።

ስለ ፡ ዝሙት ፡ ቅጣት ።

፩ሺ፯፻፹፩ ፶፱ ። የሌላውን ፡ ሰራተኛ ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ ይህ፡ በፈቃዱዋ ፡ ቢሆን ፡ የእርሱዋንና ፡ የእርሱን ፡ አፍንጫ ፡ ይፎንኑ ። እርሱዋን ፡ በማስገደድ ፡ ቢያደርግ ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ ከተቀጣ ፡ በኋላ ፡ ከገ ንዘቡ ፡ ሲሦውን ፡ ይሰጧት ።

፩ሺ፯፻፹፪ ፬ኛ ፡ ፃ፩ ፡ የታጩችውን ፡ ወይም ፡ ያልታ ጩችውን ፡ ልጃገረድ ፡ ወይም ፡ አግብቶ ፡ የፈ ታችውን ፡ ከከቡራን ፡ ወገን ፡ ብትሆን ፡ ባሪያ ፡ ወይም ፡ ነፃ ፡ የወጣች ፡ ብትሆን ፡ ይልቁንም ፡ በጠባያቸው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ልዩ ፡ ገንዘብ ፡ የሆኑትን ፡ የሚነጥቁ ፡ ይህን ፡ በኃይል ፡ ቢያደ ርጉ ፡ ይህን ፡ ያደረገ ፡ በሰይፍ ፡ ይቀጣ ። በም ንም ፡ ዓይነት ፡ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ የተባበሩ ፡ የረዱ ትም ፡ ይገረፉ ። ጠጉራቸውንም ፡ ይላጩ ። አፍንጫቸውንም ፡ ተፎንነው ፡ ይሰደዱ ። ያለጠብ ፡ ይህን ፡ ቢያደርጉ ፡ ግን ፡ የነጣቂ ፡ እጅ ፡ ብቻ ፡ ትቈረጥ ። ረዳቶቹም ፡ ይገረፉ ። የራስ ፡ ፀጉራቸውንም ፡ ተላጭተው ፡ ይሰደዱ ።

፩ሺ፯፻፹፫ ባሪያ ፡ እመቤቱን ፡ ለመንጠቅ ፡ ቢደፍር ፡ ሌላውም ፡ በዚህ ፡ ሥራ ፡ ቢረዳው ፡ በአንድ ነት ፡ በእሳት ፡ ያቃጥሏቸው ። ባሪያ ፡ ስለእመ ቤቱ ፡ መነጠቅ ፡ መከበቡዋን ፡ ቢያውቅና ፡ ባይ ረዳት ፡ ስለዚህ ፡ በእሳት ፡ ያቃጥሉት ።

፩ሺ፯፻፹፬ ፭ኛ ። ፳፩ ። በፈቃዱዋ ፡ ወይም ፡ ያለፈቃ ዱዋ ፡ ወላጆቿ ፡ ሳያውቁ ፡ ከልጃገረድ ፡ ጋር ፡ የተገናኘ ፡ ሊያገባት ፡ የሚወድ ፡ ቢሆን ፡ ለወላ ጆቿ ፡ ፈቃዱን ፡ ይፈጽሙለት ፡ ዘንድ ፡ ምርጫ፡ ይገባቸዋል ። ከወላጆቿ ፡ አንዱ ፡ እንቢ ፡ ቢል ፡ የገሠሣት ፡ ሰው ፡ ቢቻለው ፡ ባለጸጋም ፡ ቢሆን፡ ምዝን ፡ ወርቅ ፡ ይስጣት ። ባይቻለው ፡ ግን ፡ የገንዘቡን ፡ እኩሌታ ፡ ይስጣት ። በሁሉም ፡ ችጋረኛ ፡ ቢሆን ፡ ገርፈው ፡ ራሱንም ፡ ላጭ ተው ፡ ይሰደዱት ።

፩ሺ፯፻፹፭ ፮ኛ ። ከባሪያዋ ፡ ጋር ፡ ስለምትሰስን ፡ እመ ቤት ፡ ወይም ፡ ከባሪያይቱ ፡ ጋር ፡ ስለሚሰስን ፡ ጌታ ፡ ይናገራል ። ፃ፩። ባል ፡ ያላት ፡ ሴት ፡ ከባሪያ ዋ ፡ ጋር ፡ ብትሰስን ፡ ይግረፏት ። ራሱዋንም ፡ ትላ ጭ ። አፍንጫዋንም ፡ ፎንነው ፡ ከምትኖርበት ፡ ሀገር ፡ ያባርሯት ። ከመዓርጉዋም ፡ ሁሉ ፡ ትዋ ረድ ። ከእርሱዋ ፡ ጋር ፡ ለአመነዘረ ፡ ባሪያ ፡ ግን ፡ ቅጣቱ ፡ ሰይፍ ፡ ነው ።

አንቀጽ ፡ ፵፰ ።

፩ሺ፯፻፵ ዘ፵ወ፰ቱ ፡ ወብእሲት ፡ ዘእልባቲ ፡ ምት ፡ ሶበ ዘመወት ፡ ምስለ ፡ ገብራ ፡ ወኮነት ፡ ቅድመ ፡ ዘእንበለ ፡ ውሉድ ፡ ትዘበጥ ፡ ወትትላጸይ ፡ ርእሳ ፡ ወለገብርኒ ፡ ይዝብጥዎ ፡ ወይላጽይዎ ፡ ሥዕርቶ ፡ ወየሀብዎ ፡ ወይሚጥዎ ፡ ለመኰንን ፡ ወእመ ፡ ሀለዉ ፡ ላቲ ፡ ውሉድ ፡ ኵሉ ፡ ንዋያ ፡ ይኩን ፡ ለደቂቃ ፡ ወባሕቱ ፡ ታሕተ ፡ እደ ፡ ንጉሥ ፡ ይትዐቀብ ፡ ሎሙ ፡ ወተገብሮ ፡ ባሕቲቱ ፡ ይኩን ፡ ውስተ ፡ እዴሃ ፡ ወሚጠ ፡ ገብርኒ ፡ ካዕበ ፡ ይኩን ፡ ለውሉዳ ።

፩ሺ፯፻፵፩ ዘ፵ወ፩ዱ ፡ ኵሉ ፡ ዘቦ ፡ ብእሲት ፡ ወያወስባ ፡ ለእመተ ፡ ዚእሁ ፡ ሶበ ፡ ተዐውቀ ፡ ግብረ ፡ ዚእሁ ፡ ይትነሳሕ ፡ በዝብጠት ፡ ወሊቀ ፡ ሀገርኒ ፡ ይንሥእ ፡ ለይእቲ ፡ እመት ፡ ወይሚጣ ፡ ውስተ ፡ ሀገር ፡ ካልእ ፡ ወያንብር ፡ ሤጣ ፡ ውስተ ፡ መዛግብቲሁ ፡ ወዘይዜሙ ፡ በእመት ፡ ዘኢኮነት ፡ ሎቱ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ እምብዑላን ፡ የሀብ ፡ ለእጋእዝቲሃ ፡ ፴ወ፮ተ ፡ ዲናራተ ፡ ወርቅ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ እምቅሩባን ፡ ይዝብጥዎ ፡ ወየሀብ ፡ ንዋየ ፡ በእምጣነ ፡ ክሂሎቱ ፡ እምኍልቈ ፡ ፴ወ፮ቱ ፡ ዲናር ።

፩ሺ፯፻፵፪ ሳብዕ ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡ ዝሙት ። ዘ፵ወ፪ቱ ፡ ለዘማውያን ፡ ይዘብጥዎሙ ፡ ወይላጽዩ ፡ ሥዕርቶ ፡ ርእሶሙ ፡ ወይምትሩ ፡ እእናፊሆሙ ፡ ወለእለ ፡ ያስተራክብዎሙ ፡ ወይትለአክዎሙ ፡ በዝንቱ ፡ ፍኖት ፡ ይዝብጥዎሙ ፡ ወይላጽይዎሙ ፡ ወየእዝዝዎሙ ፡ ተሰዶ ፡ ወይንበሩ ፡ ብዙኀ ፡ መዋዕለ ፡ ውስተ ፡ ስደት ።

፩ሺ፯፻፵፫ ዘ፵ ፡ ብእሲ ፡ ዘቦቱ ፡ ብእሲት ፡ ወይዜሙ ፡ ይዝብጥዎ ፡ ፲ወ፪ተ ፡ ጊዜያተ ፡ በጥብጣቤ ፡ ወዘአልቦቱ ፡ ብእሲት ፡ ሶበ ፡ ደፈረ ፡ አምሳለ ፡ ዝንቱ ፡ ኃጢአት ፡ በ፯ቱ ፡ ጥብጣቤ ፡ ይነጽሕ ።

፩ሺ፯፻፵፬ ዘ፵ወ፬ቱ ፡ ኃጢአተ ፡ ዝሙት ፡ እምድኅረ ፡ ፭ቱ ፡ ዓመት ፡ ኢይትከሰስ ፡ ይኤምር ፡ ኀበ ፡ እለ ፡ ያኢብሱ ፡ እንዘ ፡ ሀለዉ ፡ ምስለ ፡ ተአዝዞ ፡ ኅሪት ፡ ኢይትፈታሕ ፡ ዘውእቱ ፡ ኀዲገ ፡ ዕዳ ፡ ምስለ ፡ ተአዝዞ ፡ ኅሩይ ።

፩ሺ፯፻፵፭ ዘ፵ወ፭ዱ ፡ ወዘተኀበለ ፡ ከመ ፡ ያንብር ፡ ፪ተ ፡ አንስተ ፡ ዘእንበለ ፡ ሕግ ፡ እላ ፡ በፈቃዱ ፡ ረኵሰ ፡ ወፈታሒ ፡ ይፍታሕ ፡ ላዕሌሁ ፡ በዝንተ ፡ ኵነኔ ፡ ዘማውያን ። ወእመ ፡ ኢያእመረት ፡ ዳግማዊት ፡ ግብራ ፡ ለቀዳማዊት ፡ ምስሌሁ ፡ ዘበሕግ ፡ ይሥረዩ ፡ ላቲ ፡

ስለ ፡ ዝሙት ፡ ቅጣት ።

፩ሺ፯፻፵ ፵፰ ። ባል ፡ የሌላት ፡ ሴት ፡ ከባሪያዋ ፡ ጋር ፡ ብታመነዝር ፡ አስቀድማ ፡ ያለልጅ ፡ ብትሆንም ፡ ትገረፍ ። ራሱዋንም ፡ ትላጭ ። ባሪያውንም ፡ ይግረፉት ። ጠጉሩንም ፡ ይላጩት ። ለዳኛም ፡ ይስጡት ፡ ወይም ፡ ይሽጡት ። ልጆች ፡ቢኖሩዋት ፡ ገንዘቡዋ ፡ ሁሉ ፡ ለልጆቿ ፡ ይሁን። ነገር ፡ ግን ፡ በዳኛ ፡ ሥልጣን ፡ ይጠበቅላቸው ። ሠርቶ ፡ የምታገኘው ፡ ብቻ ፡ በእጁዋ ፡ ይሁን ። የባሪያውም ፡ ሽያጭ ፡ ለልጆቿ ፡ ይሁን ።

፩ሺ፯፻፵፩ ፵፩ ። ሚስት ፡ ያለችው፡ ባሪያውንም ፡ የሚገናኛት ፡ ሰው ፡ ሥራዉ ፡ በታወቀ ፡ ጊዜ ፡ በግርፋት ፡ ይቀጣ ። ዳኛውም ፡ ያችን ፡ ባሪያ ፡ ወስዶ ፡ ከሌላ ፡ ሀገር ፡ ይሽጣት ። ዋጋዋንም ፡ ከዕቃቤቱ ፡ ያኑር ። የእርሱ ፡ ገንዘብ ፡ ባልሆነች ፡ ሴት ፡ ባሪያ ፡ የሚሰስን ፡ ከባለጸጎች ፡ ወገን ፡ ቢሆን ፡ ፴፮ ፡ የወርቅ ፡ ዲናር ፡ ለጌቶቿ፡ ይስጥ ። ከቅርቦች ፡ ወገን ፡ ቢሆን ፡ ይግረፉትና፡ ከ፴፮ቱ ፡ ዲናር ፡ ቍጥር ፡ ክፍሎ ፡ የተቻለውን፡ ያህል ፡ ይስጥ ።

፩ሺ፯፻፵፪ ፵፪ ። ስለዝሙት ፡ ሁሉ ፡ ይናገራል ። ፵፪ ። ዘማውያንን ፡ (አመንዝሮችን) ፡ ይግረፉዋቸው። የራሳቸውንም ፡ ፀጉር ፡ ይላጩዋቸው ። አፍንጫቸውንም ፡ ይፎንኗቸው ። በዚህም ፡ መንገድ ፡ እየተላላኩ ፡ የሚያቃጥሯቸውን ፡ ይግረፉዋቸው ። ይላጩዋቸውም ። ስደትንም ፡ ይፍረዱባቸው ። ብዙ ፡ ዘመንም ፡ በስደት ፡ ይኑሩ ።

፩ሺ፯፻፵፫ ፵ ። ሚስት ፡ ያለችው ፡ የሚያመነዝርም ፡ ሰው ፡ ፲፪ ፡ ጊዜ ፡ በጅራፍ ፡ ይግረፉት ። ሚስት፡ የሌለችው ፡ ሰው ፡ ይሆን ፡ በመሰለ ፡ ኃጢአት ፡ ቢደፍር ፡ በ፯ ፡ ግርፋት ፡ ይነጻል ።

፩ሺ፯፻፵፬ ፵፬ ። በዝሙት ፡ የተሠራ ፡ ኃጢአት ፡ ከ፭ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ አያስከስስም ። ከተመረጠች ፡ ትእዛዝ ፡ ጋር ፡ ሳሉ ፡ ስለበደሉ ፡ ሰዎች ፡ እንደሆነ ፡ ያስረዳል ። አይፈረድበትም ። ይኸውም ከተመረጠ ፡ ትእዛዝ ፡ ጋር ፡ ዕዳን ፡ መተው ፡ ነው ።

፩ሺ፯፻፵፭ ፵፭ ። እርሱ ፡ በፈቃዱ ፡ ረከሰ ፡ እንጂ ፡ ያለ ፡ ሕግ ፡ ፪ ፡ ሚስት ፡ ሊያኖር ፡ የደፈረ ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ ዳኛ ፡ የዘማውያንን ፡ ቅጣት ፡ ይፍረድበት ፡ ሁለተኛዪቱ ፡ ፊተኛዪቱ ፡ የሕግ ፡ ሚስት መሆኗን ፡ ባታውቅ ፡ ይቅርታ ፡ ያድርጉላት ።

፩ሺ፯፻፵፮ ዘ፳ወ፪ቱ ፡ ወለእመ ፡ ፀንሰት ፡ ብእሲት ፡ ወሰማሪት ፡ ከመ ፡ ታድኅስ ፡ ዘውስተ ፡ ከርሣ ፡ ያዝብጥዋ ፡ ወያስድድዋ ።

፩ሺ፯፻፵፯ ሥርዋጽ ፡ ክዑብ ፡ ሥቃዩ ፡ አውሳቢ ፡ ለውስብት ፡ እስመ ፡ ዐለዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ዐመፃሁ ፡ ለነፍሱ ፡ ወካልኡ ፡ ወያትዐወቅ ፡ ለካልኡ ፡ ብሂል ፡ መሣምርት ፡ ወመሣምርተ ፡ ካልኡ ። ወዘኢኮነ ፡ አውሳቢስ ፡ ለዘኢኮነት ፡ ውስብተ ፡ እንጋ ፡ ይኤዕምዖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በነፍሱ ፡ ባሕቲቱ ።

፩ሺ፯፻፵፰ ሳምን ፡ ዘ፳ወ፩ዱ ፡ እለ ፡ ይገብሩ ፡ ግብረ ፡ ገሞራ ፡ ለገባሪኒ ፡ ወለዘይትገበርዎ ፡ ነኪነኢሆሙ ፡ ስይፍ ። ሶበስ ፡ ኮነ ፡ ዘተገብርዎ ፡ ሕጹጸ ፡ መዋዕሊሁ ፡ እም፲ወ፪ቱ ፡ ዓመት ፡ ሕጸጸ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ያድኅኖ ፡ እምነቶኑ ።

፩ሺ፯፻፵፱ ታስዕ ፡ ዘ፳ወ፪ቱ ፡ ወእለ ፡ ይገብሩ ፡ እንስሳ ፡ ይምትሩ ፡ እስኪቶሙ ።

፩ሺ፯፻፶ ዓሥር ፡ ዘ፳ወ፫ቱ ፡ ወዘሂ ፡ አእመረ ፡ ዝሙተ ፡ ብእሲቱ ፡ ወአርመመ ፡ ይስደድ ፡ እምድኅረ ፡ ቀሠፍዎ ፡ ለዘማዊስ ፡ ወለዘማዊት ፡ ይምትሩ ፡ አእናፊሆሙ ።

፩ሺ፯፻፶፩ ክፍል ፡ ዳግማዊ ፡ በእንተ ፡ ተግሣጸ ፡ ዝሙት ፡ መንፈሳዊ ፡ ወውእቱ ፡ ፪ቱ ፡ አክፋል ። ቀዳሚ ፡ ዘካህናት ፡ ኒቅያ ፡ ዘ፲ወ፪ቱ ፡ ወለእመ ፡ ተረክበ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በምንትኒ ፡ እምዝሙት ፡ ይደቅ ፡ እመዓርጊ ፡ ክህነቱ ፡ ወኢይትመየጥ ፡ ኀቤሃ ፡ ዳግመ ፡ ወለእመ ፡ ነስሐ ፡ ኢይክልእዎ ፡ እምተደምሮ ፡ ምእመናን ፡ ወነሢአ ፡ ቍርባን ፡ እስመ ፡ ኢኮነ ፡ አበሳሁ ፡ ከመ ፡ አበሳሆሙ ፡ ለሕዝባውያን ።

፩ሺ፯፻፶፪ ዘ፲ወ፫ቱ ፡ ወለእመ ፡ ተዐቅፈ ፡ ቀሲስ ፡ ወዘመመ ፡ ወኢኮነ ፡ በቱ ፡ ልማድ ፡ እምቅድሜሁ ፡ ወኮነ ፡ ሠናየ ፡ ዜናሁ ፡ እምቅድሜሁ ፡ ወኢየሐውስዐ ፡ ብእሲተ ፡ ንስሓሁ ፡ ከመ ፡ ይጹም ፡ ወይጸሊ ፡ ዓመተ ፡ ፍጹመ ፡ ወየሀብ ፡ እምንዋዩ ፡ ምጽዋተ ፡ በአምጣነ ፡ ክሂሎቱ ፡ ወይትከላእ ፡ እመዓርገ ፡ መልእክቱ ፡ እስከ ፡ ይትፈጸም ፡ ዓመተ ፡ ንስሓሁ ። ወእምድኅረዝ ፡ ይትመየጥ ፡ ኀበ ፡ መልእክቱ ፡ ወቅዳሴሁ ፡ በከመ ፡ ነበረ ፡ ቅድመ ፡ ወይነብር ፡ በኑኀ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ዘይት

፩ሺ፯፻፵፮ ፳፪ ። ሴት ፡ ብታረግዝና ፡ በሆዷ ፡ ያለውን፡ ፅንስ ፡ ልታስወርድ ፡ ብትወድ ፡ ገርፈው ፡ የባርሯት ።

፩ሺ፯፻፵፯ ሥርዋጽ ። ባል ፡ ያላትን ፡ የደረሰ ፡ ሚስት ፡ ያለችው ፡ ሰው ፡ ኃጢአቱ ፡ ዕጥፍ ፡ ነው ። በራሱ ፡ በደል ፡ እግዚአብሔርንና ፡ ሌላውን ፡ በድሏልና ። ለካልኡ ፡ (ለሌላው) ፡ ማለት ፡ ሚስቱና ፡ የሌላው ፡ ሚስት ፡ ማለት ፡ እንደሆነ፡ ይታወቃል ። ባል ፡ ከሌላት ፡ ሴት ፡ የሚደርስ ፡ ሚስት ፡ የሌለው ፡ ግን ፡ በራሱ ፡ ብቻ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይበድለው ፡ እንደሆነ ፡ እንጂ ።

፩ሺ፯፻፵፰ ስምንተኛ ። ፳፩ ። ግብረ ፡ ሰዶም ፡ የሚሠሩ፡ ሰዎች ፡ ለአድራጊውና ፡ ለተደራጊው ፡ ቅጣታቸው ሰይፍ ፡ ነው ። ተደራጊው ፡ ፲፪ ፡ ዓመት ፡ ያልሞላው ፡ ቢሆን ፡ የዘመኑ ፡ ማነስ ፡ ከቅጣት ፡ ያድነዋል ።

፩ሺ፯፻፵፱ ዘጠኝኛ ። ፳፪ ። እንስሳን ፡ የሚገናኙ ፡ ሰዎችን ፡ ዓባለ ፡ ዘራቸውን ፡ ይቁረጡ ።

፩ሺ፯፻፶ ዐሥረኛ ። ፳፫ ። የሚስቱን ፡ ማመንዘር ፡ እያወቀ ፡ ዝም ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ከገረፉት ፡ በኋላ ፡ ይለይ ። ሴሰኛውንና ፡ ሴሰኛይቱን ፡ ግን ፡ አፍንጫቸውን ፡ ይቁረጧቸው ።

፩ሺ፯፻፶፩ ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ስለዝሙት ፡ መንፈሳዊ፡ ቅጣት ፡ ይናገራል ። ይኸውም ፡ ፪ ፡ ክፍል ፡ ነው ። መጀመሪያው ፡ የካህናት ፡ ነው ፡ ኒቅያ ፡ ፲፪ ። ኤጲስቆጶስ ፡ ከዝሙት ፡ ወገን ፡ በማናቸውም ፡ ቢገኝ ፡ ከክህነቱ ፡ መዓርግ ፡ ይሻር ። ዳግመኛም ፡ ወደእርሱዋ ፡ አይመለስ ። ንስሐ ፡ ቢገባ ፡ ግን ፡ ከምእመናን ፡ ጋር ፡ መገናኘትን ፡ ቍርባን ፡ መቀበልንም ፡ አይከልክሉት ። በደሉ ፡ እንደ ፡ ሕዝባውያን ፡ በደል ፡ አይደለምና ።

፩ሺ፯፻፶፪ ፲፫ ። ቄስ ፡ ቀስናክሎ ፡ ቢስስን ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ልማድ ፡ የሌለው ፡ ቢሆን ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮም ፡ ስም ፡ አጠራሩ ፡ መልካም ፡ ቢሆን ፡ ሚስት ፡ ያላገባም ፡ ከሆነ ፡ ንስሐው ፡ ፩ ፡ ዓመት ይጾምና ፡ ይጸልይ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ከገንዘቡም ፡ የተቻለውን ፡ ያህል ፡ ምጽዋት ፡ ይስጥ ። የንስሓው ፡ ዓመት ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ከክህነት ፡ ሥራው ፡ ይከልከል ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ቀድሞ ፡ እንደነበረ ፡ ወደአገልግሎቱና ፡ ወደቅዳሴው ፡ ይመለስ ። በዘመኑም ፡ ሁሉ ፡ እድግ ፡ የሚጠነቀቅ

ዘተቀብ ፡ ጥቀ ። ወለእመ ፡ ተመይጠ ፡ ድኅረ ፡ ንስሐሁ ፡ ወገብረ ፡ በአምሳለ ፡ ዝንቱ ፡ ይጻእ ፡ እምክህነቱ ፡ ባሕቱ ፡ ኢይክልእዎ ፡ እምተሳትፎ ፡ ምእመናን ፡ ወቍርባን ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘአውሰበ ፡ ወብእሲቱኒ ፡ ምስሌሁ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡ ይግበሩ ፡ ቦቱ ፡ በአምሳለ ፡ ዝንቱ ፡ ካዕበተ ፡ ዘከመ ፡ ቀዳሚ ፡ ንስሓ ።

፩ሺ፯፻፵፫ ወዲያቆንኒ ፡ ይኩን ፡ በቀዳሚ ፡ በአምሳለ ፡ ቀሲስ ፡ ወለእመ ፡ ተመይጠ ፡ በጻማም ፡ ንስሐሁ ፡ ፩፯ ፡ ዓመት ፡ ወእመ ፡ ተመይጠ ፡ በካልስ ፡ ይጻእ ፡ እምክህነቱ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ብእሲት ፡ ወእመኒ ፡ ሀለውት ፡ ብእሲቱ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡ ይትኀደግ ፡ በንስሐ ፡ ድኅረ ፡ ተሰደ ፡ ፲ተ ፡ ዓመተ ፡ ወበፍጻሜ ፡ ፲ቱ ፡ ዓመት ፡ ይትመየጥ ፡ ኀበ ፡ ክህነቱ ፡ ወእመሰ ፡ ተመይጠ እምድኅረዝ ፡ ይጻእ ፡ እምክህነቱ ፡ ግሙረ ። ወፈድፋደሰ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ይጻእ ፡ ፍጹመ ፡ እመ ዓርገ ፡ በአበሳሁ ፡ ቀዳማዊ ፡ ወአልቦቱ ፡ ንስሓ ፡ ዳእሙ ፡ ኢይክልእዎ ፡ እምተሳትፎተ ፡ ምእመናን ፡ ወነሢአ ፡ ቍርባን ።

፩ሺ፯፻፵፬ ወቀሲስኒ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ብእሲት ፡ ይነስሕ ፡ ወዘሰ ፡ ቦቱ ፡ ብእሲት ፡ ኢይነስሕ ።

፩ሺ፯፻፵፭ ወዲያቆንኒ ፡ ዘአልቦቱ ፡ ብእሲት ፡ ይነስሕ ፡ ፪ተ ፡ ጊዜያተ ፡ ወዘቦቱ ፡ ብእሲት ፡ ፩ደ ፡ ጊዜ ፡ ወኢይክልእዎሙ ፡ እምነሢአ ፡ ቍርባን ፡ ወተሳትፎተ ፡ ምእመናን ፡ አላ ፡ ይክልእዎሙ ፡ እምተልእኮ ፡ ምሥዋዕ ።

፩ሺ፯፻፵፮ ወለእለ ፡ ተርፉሰ ፡ ካህናት ፡ ወመነኮሳት ፡ ወሕዝባውያን ፡ ለእመ ፡ አበሱ ፡ በአምሳለ ፡ ዝንቱ ፡ አበሳ ፡ ይፍትሖ ፡ ሳዕሌሆሙ ፡ ሊቀ ፡ ምኔት ፡ ወረድኤት ፡ ዘከመ ፡ ይደሉ ፡ ለንስሓ ሆሙ ፡ ባሕቱ ፡ ኢያክብዱ ፡ ቦሙ ፡ ክበደ ፡ ንስሓ ፡ ጽኑዐ ፡ ከመ ፡ ኢይትኀጐሉ ፡ ወኢይትኀ ድጉ ፡ ክዕበ ፡ ወኢይትጓወርዎሙ ፡ ከመ ፡ ኢይ ግበኡ ፡ ውስተ ፡ ቀዳሚሆሙ ፡ ወኃጢአቶሙ ፡ ወኢይትመክዐብ ፡ ኀጕሎሙ ፡ ወዘአበየ ፡ ዘንተ ትእዛዘ ፡ ሲኖዶስ ፡ ታውግዞ ።

፩ሺ፯፻፵፯ ዳግም ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ተርፉ ፡ ምእመናን ። ኒቅያ ፡ ዘ፸ወ፬ቱ ፡ እመቦ ፡ ብእሲ ፡ ምእመን ፡ ዘዮተሉ ፡ ብእሲተ ፡ እንተ ፡ ኢተአምን ፡ አው ፡ ብእሲት ፡ ማእምንት ፡ ዘትተሉ ፡ ብእሲ ፡ ዘኢየ

ይሁን ። ከንስሐውም ፡ በኋላ ፡ ተመልሶ ፡ ይህን፡ የመሰለ ፡ ሥራ ፡ ቢሠራ ፡ ከክህነቱ ፡ ይሻር ። ነገር ፡ ግን ፡ ከምእመናን ፡ አንድነትና ፡ ከቍር ባን ፡ አይከልክሉት ። ያገባ ፡ ቢሆን ፡ ሚስቱም፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ብትኖር ፡ በዚህ ፡ ምሳሌ ፡ እንደ መጀመሪያው ፡ ንስሓ ፡ ዕጥፍ ፡ ያድርጉበት ።

፩ሺ፯፻፵፫ ዲያቆንም ፡ በመጀመሪያ ፡ እንደ ፡ ቄስ ፡ ይሁን ። ቢመለስም ፡ በሁለተኛው ፡ ንስሓው ፡ ፩ ፡ ዓመት ፡ ይሁን ። በ፫ኛ ፡ ቢመለስ ፡ ከክህ ነቱ ፡ ይሻር ። ሚስት ፡ የሌለችው ፡ ከሆነ ። ሚ ስቱ ፡ በቤቱ ፡ ካለች ፡ ፲ ፡ ዓመት ፡ ከተለየ ፡ በኋላ ፡ በንስሐ ፡ ይቅርለት ። በ፲ ፡ ዓመት ፡ መጨ ረሻም ፡ ወደክህነቱ ፡ ይመለስ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቢመለስ ፡ ግን ፡ ፈጽሞ ፡ ከክህነቱ ፡ ይሻር ። ይልቁንም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በመጀመሪያ ፡ ኀጢ አቱ ፡ ከሹመቱ ፡ ፈጽሞ ፡ ይሻር ። ከምእመናን ፡ ጋር ፡ ከመገናኘት ፡ ቍርባን ፡ ከመቀበል ፡ አይከ ልክሉት ፡ እንጂ ፡ ንስሓ ፡ የለውም ።

፩ሺ፯፻፵፬ ሚስት ፡ የሌለችውም ፡ ቄስ ፡ በንስሐ ፡ ይመ ለስ ። ሚስት ፡ ያለችው ፡ ግን ፡ በንስሓ ፡ አይመ ለስ ።

፩ሺ፯፻፵፭ ሚስት ፡ የሌለችው ፡ ዲያቆንም ፡ ፪ት ፡ ጊዜ ፡ ሚስት ፡ ያለችው ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በንስሐ ፡ ይመለስ ። ቍርባን ፡ ከመቀበልና ፡ ከምእመናን፡ አንድነት ፡ አይከልክሏቸው ። ከመቅደስ ፡ አገ ልግሎት ፡ ይከልክሏቸው ፡ እንጂ ።

፩ሺ፯፻፵፮ የቀሩት ፡ ካህናትና ፡ መነኮሳት ፡ ሕዝባውያ ንም ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ በደል ፡ ቢበድሉ ፡ አበ ምኔቱና ፡ ዳኛ ፡ ለንስሓቸው ፡ እንደሚገባ ፡ ይፍረዱባቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ እንዳይጎዱ ፡ ዳግመ ኛም ፡ እንዳይተዉ ፡ ቀኖናውን ፡ ዕጉ ፡ አድርገው አያክብዱባቸው ። ወደቀደመ ፡ ጥፋታቸውና ፡ ኃጢአታቸው ፡ እንዳይመለሱ ፡ ቸል ፡ አይበ ሏቸው ። ጥፋታቸውም ፡ ዕፅፍ ፡ ድርብ ፡ እን ዳይሆን ፡ ይህን ፡ ትእዛዝ ፡ አልቀበልም ፡ ያለ ውንም ፡ ሲኖዶስ ፡ ታወግዘዋለች ። (ትለየዋ ለች) ።

፩ሺ፯፻፵፯ ሁለተኛው ፡ ስለቀሩት ፡ ምእመናን ፡ ይናገ ራል ። ኒቅያ ፡ ፸፬ ። ያላመነችውን ፡ ሴት ፡ የሚ ከተል ፡ አማኒ ፡ ወንድ ፡ ቢኖር ፡ ወይም ፡ እንዲሁ፡ ለአንዱ ፡ ከሃይማኖት ፡ ለመውጣት ፡ ምክን

አንቀጽ ፡ ፵፰ ።

አምን ፡ በምክንያተ ፡ ዝሙት ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ እሐዱ ፡ ለካልኡ ፡ ምክንያተ ፡ ወዓእ እምሃይማኖት ፡ ንስሐሆሙ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ተቀዪም ፡ በአንቀጸ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ፫ተ ፡ ዓመተ ፡ በለቢሰ ፡ ሠቅ ፡ ወነጺረ ፡ ሐመድ ። ወእምድኅረ ፡ ዝ ፡ ይባኡ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በባሕቲቶሙ ፡ ተራሲዮሙ ፡ ፩ደ ፡ ዓመተ ፡ ወኢይሳተፍዎሙ ፡ ሰብአ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በእማኁ ፡ ወቍርባን ። ወእምድኅረ ፡ ፍጻሜ ፡ ዓመት ፡ ይባርክ ፡ ቀሲስ ፡ ላዕለ ፡ ማይ ፡ ወዘይት ፡ በካልእ ፡ እምልማደ ፡ ጥምቀት ፡ እንበለ ፡ ቅብዐ ፡ ሜሮን ፡ አላ ፡ ከመ ፡ ልማደ ፡ ቡራኬ ፡ በላዕለ ፡ ማይ ፡ ወቅብዕ ፡ በእንተ ፡ ድዉያን ። ወእምዝ ፡ ይነዝኀ ፡ ካህን ፡ እምውእቱ ፡ ማይ ፡ ወይነዝኆ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ወእሙንቱ ፡ እንዘ ፡ ይትአመኑ ፡ ወየኀድጉ ፡ ኃጢአቶሙ ፡ ወይትገነዩ ፡ ለሙ ፡ በጸሎት ። ወእምድኅረዝ ፡ የሀብዎሙ ፡ እምቍርባን ፡ ወዘተዐደወ ፡ ዘንተ ፡ ትእዛዘ ፡ ሲኖዶስ ፡ ያወግዝ ።

፩ሺ፯፻፵፰ ረስጠጅ ፡ ፳ወ፪ቱ፡ ረስጠብ ፡ ፵ወ፯ቱ ፡ እመቦ ፡ ሕዝባዊ ፡ ዘነሥአ ፡ ለድንግል ፡ ዘእሑፀት ፡ ለካልኡ ፡ ወተንሥአ ፡ ላዕሌሃ ፡ ይትፈለጥ ፡ ወኢያውስብ ፡ ካልእተ ፡ ዘእንበሌሃ ፡ አላ ፡ ያውስብ ፡ ኪያሃ ፡ በከመ ፡ አፍቀራ ፡ እመኒ ፡ ኮነት ፡ ሕሥምተ ፡ አው ፡ ነዳይተ ።

፩ሺ፯፻፵፱ ዘዕንቀራ ፡ ፲ወ፱ቱ ፡ ወዘኒ ፡ ዘመወ ፡ ምስለ ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ምት ፡ ይደሉ ፡ ላዕሌሁ ፡ ከመ ፡ የአንግዝ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ዘውእቱ ፡ ፯ቱ ፡ ዓመት ፡ በከመ ፡ አቅደምነ ።

፩ሺ፯፻፶ በስ ፡ ፲ወ፪ቱ ፡ ወዘቦቱ ፡ ብእሲት ፡ ለእመ ፡ ዘመወ ፡ ይቁም ፡ ፪ተ ፡ ዓመተ ፡ በአፍአ ። ወእመ ፡ ገብረ ፡ እምቅድመ ፡ ያውስብ ፡ ብእሲተ ፡ ንስሐሁ ፡ ፯ቱ ፡ ሰባዒ ፡ ወይገሥጽዎ ፡ ከመ ፡ ያውስብ ፡ ብእሲተ ፡ ወለእመ ፡ ኢፈቀደ ፡ አውስቦ ፡ ይስደድ ፡ እስከ ፡ ያወስብ ፡ ወእመ ፡ አኮ ፡ ይትገኀሥ ፡ እምዝሙት ።

፩ሺ፯፻፶፩ ዘ፲ወ፫ቱ ፡ ወዘኒ ፡ ዘመወት ፡ ብእሲቱ ፡ ለእመ ፡ ኢያእመረ ፡ ይደልዋ ፡ ኵነኔ ፡ ንስሓ ፡ ለባሕቲታ ። ወእመ ፡ አእመረ ፡ ወኢፈቀደ ፡ አውስቦታ ፡ ይትፈለጡ ፡ ክልኤሆሙ ። ዘ፲ወ፬ቱ ፡ ወእመ ፡ ኮነ ፡ ካህነ ፡ ይደቅ ፡ እመንበሩ ፡ ወይትገኀሥ ፡ እምተመጥዎተ ፡ ምሥጢር ፡

ስለ ፡ ዝሙት ፡ ቅጣት ።

ያት ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ በዝሙት ፡ ምክንያት ፡ ያላመነ ፡ ወንድን ፡ የምትከተል ፡ አማኒት ፡ ሴት ፡ ብትኖር ፡ ንስሓቸው ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ማቅ ፡ በመልበስና ፡ አመድ ፡ በመነስነስ ፡ በአንቀጸ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መቆም ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ብቻቸውን ፡ ተለይተው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይግቡ ። የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰዎችም ፡ እጅ ፡ በመንሣሣትና ፡ በቍርባን ፡ አይገናኟቸው ። ዓመቱም ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ያለሜሮን ፡ ከጥምቀት ፡ ልማድ ፡ ልዩ ፡ በሆነ ፡ በውሃና ፡ በዘይት ፡ ላይ ፡ ቄስ ፡ ይባርክ ። ስለድውያን ፡ በውሃና ፡ በዘይት ፡ ላይ ፡ እንደሚያደርገው ፡ ያለ፡ እንደቡራኬ ፡ ልማድ ፡ ነው ፡ እንጂ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ቄሱ ፡ ከዚያ ፡ ውሀ ፡ እየታፈነ ፡ ይርጫቸው ። እነርሱም ፡ ኃጢአታቸውን ፡ እያመኑ ፡ ይተዋሉ ። በጸሎትም ፡ ይሠረይላቸዋል ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከቍርባን ፡ ይስጧቸው ። ይህን ፡ ትእዛዝ ፡ ያፈረሰውንም ፡ ሲኖዶስ ፡ ያወግዘዋል ። (ይለየዋል )።

፩ሺ፯፻፵፰ ረስጠጅ ፡ ፳፪ ። ረስጠብ ፡ ፵፯ ። ያላጩለትን ፡ ልጃገረድ ፡ የነጠቀ ፡ ሕዝባዊ ፡ ቢኖር ፡ ቢደፋፈራትም ፡ ይለይ ። ከእርሱዋም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አያግባ ። መልከ ፡ ክፉም ፡ ብትሆን ፡ ደኃም ፡ ብትሆን ፡ እንደ ፡ ወደዳት ፡ እርሱዋን ፡ ያግባ ።

፩ሺ፯፻፵፱ ዕንቀራ ፡ ፲፱ ። ባል ፡ ካላት ፡ ሴት ፡ ጋራ ፡ ያመነዘረ ፡ ወንድ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ንስሓ ፡ ሊገባ ፡ ይገባዋል ። ይኸውም ፡ አስቀድመን ፡ እንደተናገርን ፡ ፯ ፡ ዓመት ፡ ነው ።

፩ሺ፯፻፶ በስ ፡ ፲፪ ። ሚስት ፡ ያለችው ፡ ሰው ፡ ቢሰስን ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ በአፍኣ ፡ ይቁም ። ሚስት ፡ ከማግባቱ ፡ በፊት ፡ ቢያመነዝር ፡ ግን ፡ ንስሐው ፡ ፯ ፡ ሱባኤ ፡ ነው ። ሚስትም ፡ እንዲያገባ ፡ ይምከሩት ። ማግባትንም ፡ ባይወድ ፡ እስኪያገባ ፡ ድረስ ፡ ይለይ ። ያም ፡ ባይሆን ፡ ከዝሙቱ ፡ ይከልከል ።

፩ሺ፯፻፶፩ ፲፫ ። ሚስቱ ፡ የሰሰነችበት ፡ ሰው ፡ ባያውቅ ፡ ለብቻዋ ፡ የንስሓ ፡ ቅጣት ፡ ይገባታል ። በውቆ፡ ሊፈታት ፡ ባይወድ ፡ ግን ፡ ሁለቱም ፡ ይለዩ ። ፲፬ ። ካህን ፡ ቢሆን ፡ ከሹመቱ ፡ ይሻር ። ምሥጢርንም ፡ ከመቀበል ፡ ይራቅ ። (ይከልከል ። ተጸጽቶ ፡ ቢፈታት ፡ ግን ፡ ከምሥጢር ፡ ይስጡት ፤

ወሶበ ፡ ነስሐ ፡ ወአውፅአ ፡ የዘብዎ ፡ እምሥጢር ፡ ባሕቱ ፡ ኢይትመየጥ ፡ ኀበ ፡ መዓርጉ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ተሳተፈ ፡ ዘማዊተ ።

፩ሺ፯፻፶፪ ኀልስ ፡ በእንተ ፡ ዘይሴሙ ፡ ምስለ ፡ እለ ሕሩም ፡ አውስቦቶን ። በስ ፡ ዘጸወረቱ ፡ ወዘኒ ፡ ይሴሙ ፡ በወለተ ፡ ብእሲቱ ፡ ይፃእ ፡ ፲ወ፰ተ ፡ ዓመተ ፡ ፮ተ ፡ ዓመተ ፡ እንዘ ፡ ይበኪ ፡ ወ፩ተ ፡ ዓመተ ፡ እንዘ ፡ ይሰምዕ ፡ ቃለ ፡ ምዕዳን ፡ ወ፰ተ ፡ ዓመተ ፡ ተቀዊሞ ፡ ምስለ ፡ ምእመናን ።

፩ሺ፯፻፶፫ ዘጸወ፬ቱ ፡ ወዘይሴሙ ፡ በእኅተ ፡ ብእሲቱ ፡ ይፃእ ፡ ፲ወ፩ተ ፡ ዓመተ ፡ ወከማሁ ፡ ብእሲትኒ ፡ እንተ ፡ ዘመወት ፡ በ፪ቱ ፡ አኀው ።

፩ሺ፯፻፶፬ ዘጸወ፰ቱ ፡ ወዘአውስበ ፡ ፪ተ ፡ አኃተ ፡ ከማሁ ፡ ብእሲትኒ ፡ ዘትትወሰብ ፡ ለ፪ቱ ፡ አኀው ይትፈለጡ ፡ ወይኩኑ ፡ ታሕተ ፡ ሥርዐተ ፡ ንስሓ ፡ ወኢይሳተፍዎሙ ፡ እምዕሩ ፡ በለዉ ፡ በዝንቱ ።

፩ሺ፯፻፶፭ ራብዕ ፡ በስ ፡ ዘ፲ወ፯ቱ ፡ እመ ፡ ፈቀደት ፡ ብእሲት ፡ ዘማዊት ፡ ከመ ፡ ትነስሕ ፡ ትወልጥ ፡ አልባሲሃ ፡ ወታሰስል ፡ ሠርጐ ፡ ዝሙታ ፡ ወትቁም ፡ ዓመተ ፡ ፍጹመ ፡ እንዘ ፡ ይምዕድዋ ፡ ውስተ ፡ አንቀጸ ፡ እምቅድመ ፡ ትደለው ፡ ለተሳትፎ ፡ ምስለ ፡ መርዓተ ፡ ክርስቶስ ። ወእምድኅረ ፡ ዝንቱ ፡ ትቁም ፡ ካዕበ ፡ ፰ተ ፡ አውራኀ ፡ እንዘ ፡ ትሰምዕ ፡ ቃላተ ፡ ወትወፅእ ፡ ምስለ ፡ ንኡሰ ፡ ክርስቲያን ፡ ወ፬ተ ፡ አውራኀ ፡ ቀዊማ ፡ ምስለ ፡ ምእመናት ፡ ወእምድኅረ ፡ ፍጻሜ ፡ ዓመት ፡ ትትመጠው ፡ እምሥጢር ፡ ቅዱስ ። ወለእመስ ፡ ኮነት ፡ ዘኢተጠምቀት ፡ ወፈተወት ፡ ከመ ፡ ትነስሕ ፡ እምዝሙታ ፡ ይገሥጽዋ፡ ፵ ፡ መዋዕለ ፡ ወይትሐበይዋ ፡ ወትጠመቅ ።

፩ሺ፯፻፶፮ ሥርዐጸ ፡ ሕገ ፡ ገሞራውያን ፡ ይንበሩ ፡ በነኮሉ ፡ ሕይወቶሙ ፡ ምስለ ፡ መስተብቋዕያን ።

፩ሺ፯፻፶፯ ኃምስ ፡ ዕንቆራ ፡ ዘ፲ወ፰ቱ ፡ ወዘይሴሙ ፡ በእንስሳ ፡ ወነኮሉ ፡ ዘይገብር ፡ ኃጢአተ ፡ ቅድመ ፡ ይብጻሕ ፡ ኀበ ፡ ፳ ፡ ዓመት ፡ ሶበ ፡ ነበሩ ፡ ፲ወ፰ተ ፡ ዓመተ ፡ እንዘ ፡ ይትጌሠጹ ፡ ይሳተፍዎሙ ፡ በጸሎት ፡ እምድኅረ ፡ ፲ወ፭ቱ ፡ ዓመት ፡ ወይትመጠዉ ፡ እምሥጢር ፡ ቅዱስ ፡ እምድኅረ ፡ ሐተቱ ፡ ግብሮሙ ።

፩ሺ፯፻፶፰ ሳድስ ፡ ረስጠጅ ፡ ፵ወ፱ቱ ፡ ዘይበልዕ ፡ ምስለ ፡ ዘማውያን ፡ ይትገኀሥ ፡ ወአመአኮ ፡ ይሰደድ ።



ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ መዓርጉ ፡ አይመለስ ። እርሱ ፡ ከአመንዝራይቱ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ሁኗልና ።

፩ሺ፯፻፶፪ ፫ኛው ። ጋብቻቸው ፡ ከተከለከለ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ስለሚሰስን ፡ ሰው ፡ ይናገራል ። በስ ፡ ፳፫፡ በሚስቱ ፡ ልጅ ፡ ያመነዘረ ፡ ፲፰ ፡ ዓመት ፡ ይለይ ። ፮ ፡ ዓመት ፡ እያለቀሰ ፡ ፬ ፡ ዓመት ፡ ቃለ ምዕዳን ፡ እየሰማ ፡ ፰ ፡ ዓመት ፡ ከምእመናን ጋር ፡ ቆሞ ።

፩ሺ፯፻፶፫ ፳፬ ። በሚስቱ ፡ እኅት ፡ የሚያመነዝር ፡ ፲፩ ዓመት ፡ ይለይ ። በሁለት ፡ ወንድማማቾች ያመነዘረች ፡ ሴትም ፡ እንደዚሁ ።

፩ሺ፯፻፶፬ ፳፰ ። ሁለት ፡ እትማማቾችን ፡ ያገባ ፡ እንደዚሁም ፡ ሁለት ፡ ወንድማማቾችን ፡ ያገባች ፡ ሴት ፡ ይለዩ ። በዕኑ ፡ ቀኖናም ፡ ይቀጡ ። በዚህ፡ ሳሉም ፡ አይገናኝዋቸው ።

፩ሺ፯፻፶፭ ፬ኛ ። በስ ፡ ፲፯ ፡ አመንዝራ ፡ ሴት ፡ ልትመለስ ፡ ብትወድ ፡ የዝሙት ፡ ጌጧን ፡ ጥላ ፡ ልብሱዋን ፡ ትለውጥ ። ከክርስቶስ ፡ መንጋዎችም ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ለመሆን ፡ ከመብቃቷ ፡ በፊት ፡ እየመከሯት ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ በአፍአ ፡ ትቁም ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ምዕዳን ፡ ሰምታ ፡ ከንኡስ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋር ፡ እየወጣች ፡ ፰ ፡ ወር ፡ ትቆይ ። ፬ ፡ ወርም ፡ ከምእመናት ፡ ሴቶች ጋራ ፡ እየቆመች ፡ ቆይታ ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ከቅዱስ ፡ ቁርባን ፡ ትቀበል ። ያልተጠመቀች ፡ ብትሆን ፡ ግን ፡ ከዝሙትዋም ፡ ልትመለስ ፡ ብትወድ ፡ ፵ ፡ ቀን ፡ ይምከርዋት ። ያስተምርዋትናም ፡ ትጠመቅ ።

፩ሺ፯፻፶፮ ሥርዋጽ ። ግብረ ፡ ሰዶም ፡ የሚሠሩ ፡ ሰዎች፡ በዘመናቸው ፡ ሁሉ ፡ ከአማላጆች ፡ ጋራ ፡ ይኑሩ

፩ሺ፯፻፶፯ ፭ኛ ። ዕንቆራ ፡ ፲፰ ። በእንስሳ ፡ የሚያመነዝር ፡ ፳ ፡ ዓመት ፡ ከመሙላቱ ፡ አስቀድሞ ፡ ኃጢአት ፡ የሠራ ፡ ሁሉም ፡ ፲፰ ፡ ዓመት ፡ ሲመከሩ ፡ ቆይተው ፡ ከ፲፭ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ በጸሎት ይገናኝዋቸው ። ሥራቸውንም ፡ ከመረመሩ ፡ በኋላ ፡ ከቅዱስ ፡ ቍርባን ፡ ይቀበሉ ።

፩ሺ፯፻፶፰ ፮ኛ ። ረስጠጅ ። ፵፱ ። ከአመንዝሮች ፡ ጋራ ፡ የሚበላ ፡ ይከልከል ። ያለዚያም ፡ ይለይ ።

## አንቀጽ ፡ ፶ወ፱ቱ ፡

### በእንተ ፡ ኩነኔ ፡ ሰረቀት ፡ ሥጋዊ ፡ ወመንፈሳዊ ።

፩ሺ፯፻፶፱ ቀዳማዊ ፡ በከመ ፡ ተነግረ ፡ ውስተ ፡ መጽሐፍ ፡ ዳግም ፡ እምአሪት ፡ ወይቤ ፡ እመቦ ፡ ብእሲ ፡ ዘሰረቀ ፡ ላሕመ ፡ አው ፡ በግዐ ፡ ወጠብሖሙ ፡ አው ፡ ሤጦሙ ፡ ይፍዲ ፡ ህየንተ ፡ ፩ዱ ፡ ላሕም ፡ ፭ተ ፡ እደ ፡ ወህየንተ ፡ ፩ዱ ፡ በግዕ ፡ ፬ተ ፡ እደ ። ወለእመኒ ፡ ኢተረክበ ፡ በኀቤሁ ፡ ዘሰረቆ ፡ ወእመኒ ፡ ኢሀለዎ ፡ ንዋዩ ፡ ይሚጥዎ ፡ በእንተ ፡ ዘሰረቀ ። ወለእመ ፡ ተረክበ ፡ ዘተሰርቀ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ እመሂ ፡ ላሕም ፡ አው ፡ አድግ ፡ አው ፡ በግዕ ፡ ሕያዋኒሆሙ ፡ የሀብ ፡ ህየንተ ፡ ፩ዱ ፡ ፪ኤተ ።

፩ሺ፯፻፷ ወለእመ ፡ ኢዐቀበ ፡ ብእሲ ፡ እንስሳሁ ፡ ወበልዐ ፡ እምገራህተ ፡ ካልኡ ፡ የሀብ ፡ ህየንተ ፡ ውእቱ ፡ ዘይሤኒ ፡ እምፍሬያተ ፡ ዘርኡ ።

፩ሺ፯፻፷፩ ወበአሪት ፡ ኃምስ ፡ ይብል ፡ እመ ፡ ተረክበ ፡ ብእሲ ፡ ዘሰረቀ ፡ ነፍሰ ፡ እምአኃዊሁ ፡ ወእመሂ ፡ ረሰየ ፡ ከመ ፡ ይስርቁ ፡ አው ፡ ሤጠ ፡ ይደልዎ ፡ ሞት ፡ ለሰራቂ ።

፩ሺ፯፻፷፪ ወበቀኖና ፡ ነገሥት ፡ ንቡር ፡ ዘ፭ቱ ፡ አክፋል ፡ ቀዳማዊ ፡ ጠስ ፡ ዘ፴ወ፱ቱ ፡ እመቦ ፡ ብእሲ ፡ ዘይበውእ ፡ ውስተ ፡ ምሥዋዕ ፡ መዓልተ ፡ አው ፡ ሌሊተ ፡ ወይነሥእ ፡ እምዘውስቴቱ ፡ ምንተኒ ፡ ይዝሕልዎ ፡ በሐጺን ፡ ርሱን ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ በአፍአ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይዝብጥዎ ፡ ወይላጽይዎ ፡ ርእሶ ፡ ወይሰድድዎ ።

፩ሺ፯፻፷፫ ዳግም ፡ መክ ፡ ዘ፪ወ፲ቱ ፡ ወ፪፻ወ፩ዱ ፡ እለ ፡ ይሰርቁ ፡ ሕፃናተ ፡ እመኒ ፡ ኮኑ ፡ እግብርተ ፡ አው ፡ እግዓዝያን ፡ ወእመቦ ፡ እምሕዝብ ፡ እለ ፡ ኃለፉ ፡ ሀገረ ፡ ወነድኡ ፡ እምኔሃ ፡ እንስሳ ፡ እምአፍራስ ፡ ወአልሕምት ፡ ተባዕተ ፡ አው ፡ አንስተ ፡ እስመ ፡ ሕግነ ፡ ትኤዝዝ ፡ ከመ ፡ ይቅትልዎሙ ፡ አው ፡ ከመ ፡ ይስደድዎሙ ፡ እስከ ፡ አጽናፈ ፡ ምድር ። ወግብሮሙ ፡ ብዉሕ ፡ ለፈታሒ ፡ ከመ ፡ ይፍድዮሙ ፡ በእምጣነ ፡ ሐሳበ ፡ አበሳሆሙ ፡ እመሂ ፡ ዐቢይ ፡ አው ፡ ንኡስ ፡ ውእቱ ።



## አንቀጽ ፡ ፶፱ ።

### ስለ ፡ ሌቦች ፡ ሥጋዊና ፡ መንፈሳዊ ፡ ቅጣት ፡ ይናገራል ።

፩ሺ፯፻፶፱ መጀመሪያው ፡ ከኦሪት ፡ በ፪ኛው ፡ መጽሐፍ እንደተነገረ ፡ ነው ። እንዲህም ፡ አለ ። ላም ወይም ፡ በግ ፡ የሰረቀ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ቢያርዳ ዳቸው ፡ ቢሸጣቸውም ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ ላም እምስት ፡ እጅ ፡ ስለአንድ ፡ በግዕም ፡ ፬ ፡ እጅ አድርጎ ፡ ይክፈል ። የሰረቀው ፡ ገንዘብም በእጁ ፡ ባይገኝ ፡ ገንዘብም ፡ ባይኖረው ፡ ስለሰረ ቀው ፡ ገንዘብ ፡ ይሽጡት ። የሰረቀው ፡ ገንዘብ ላም ፡ ወይም ፡ አህያ ፡ ወይም ፡ በግ ፡ ቢሆን ደኅና ፡ ሆኖ ፡ በእጁ ፡ ቢገኝ ፡ ስለ ፡ አንዱ ፈንታ ፡ ሁለት ፡ አድርጎ ፡ ይስጥ ። (ዘፀ ፡ ፳፪ ፩ - ፭) ።

፩ሺ፯፻፷ ሰው ፡ እንስሳዉን ፡ ባይጠብቅ ፡ የሌላውንም አዝመራ ፡ ቢበላ ፡ ስለዚህ ፡ ፈንታ ፡ ግምቱን ከእርሱ ፡ አዝመራ ፡ ያማረውን ፡ ይስጥ ። (ዘፀ ፳፪ ፡ ፭ - ፮) ።

፩ሺ፯፻፷፩ በአምስተኛው ፡ ኦሪትም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ከወንድሞቹ ፡ ሰው ፡ የሰረቀ ፡ ቢገኝ ፡ ወይም ለሌቦች ፡ እንዲሰርቁ ፡ ቢያደርግ ፡ ወይም ቢሸጥ ፡ ለሌባው ፡ ሞት ፡ ይገባዋል ። (ዘዳ ፳፬ ፡ ፯) ።

፩ሺ፯፻፷፪ በፍትሐ ፡ ነገሥትም ፡ አምስት ፡ ክፍል ተጽፏል ። መጀመሪያው ፡ ጠስ ፡ ፴፱ ። በቀን ወይም ፡ በሌሊት ፡ ከቤተ ፡ መቅደስ ፡ ገብቶ በውስጡዋ ፡ ካለው ፡ ማናቸውንም ፡ የወሰደ ቢኖር ፡ በጋለ ፡ ብረት ፡ ይተኩሱት ። ከቤተ ክርስቲያንም ፡ በአፍኣ ፡ ቢሆን ፡ ይግረፉት ራሱንም ፡ ላጭተው ፡ ይለዩት ።

፩ሺ፯፻፷፫ ሁለተኛውም ፡ መክ ፡ ፪፲ ፡ ፪፻፩ ። ሕፃናትን የሚሰርቁ ፡ ባሮች ፡ ወይም ፡ የጨዋ ፡ ልጆች ቢሆኑ ፡ ከሕዝቡ ፡ ወገን ፡ ወደሌላ ፡ ሀገር ፡ ሄ ው ፡ ወንድ ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ከፈረሶችና ፡ ከላ ች ፡ ከእርስዋ ፡ እንስሳትን ፡ የነዱ ፡ ቢኖሩ ፡ ይ ድሏቸው ፡ ዘንድ ፡ ወይም ፡ እስከ ፡ ምድር ፡ ዳርቻ ድረስ ፡ ያሳድዷቸው ፡ ዘንድ ፡ ሕጋችን ፡ ታዝዛለች እኮ ። ዳኛም ፡ ሥራቸውን ፡ ሊመረምር ፡ ይገ ዋል ። ትልቅ ፡ ወይም ፡ ትንሽ ፡ ቢሆን ፡ በበደ ቸው ፡ ግምት ፡ ልክ ፡ ይፈርድባቸው ፡ ዘንድ ።

አንቀጽ ፡ ፵፱ ።

፩ሺ፯፻፺፬ ጠስ ፡ ፴ወ፱ቱ ፡ እለሂ ፡ ይነድኡ ፡ መርዔተ ፡ ዘኢኮነ ፡ ሎሙ ፡ በቀዳሚ ፡ ጊዜ ፡ ይዝብጥዎሙ ፡ ወበዳግም ፡ ይሰድድዎሙ ፡ ወበሣልስ ፡ ይምትሩ ፡ እደዊሆሙ ፡ ወመርዔት ፡ ይግባእ ፡ ኀበ ፡ እግዚኡ ።

፩ሺ፯፻፺፭ ሣልስ ፡ ጠስ ፡ ዘ፴ወ፱ቱ ፡ ወዘይከውን ፡ መኰንን ፡ ሬዲተ ፡ ቀታሊ ፡ ትትመተር ፡ እዴሁ ፡ ወእደወ ፡ እለ ፡ ይረድእዎ ። ወለእለሂ ፡ ይሰርቁ ፡ እምትዕይንት ፡ እመ ፡ ኮነ ፡ ዘሰረቅዎ ፡ እምንዋየ ፡ ሐቅል ፡ ባሕቲቱ ፡ ይዝብጥዎሙ ፡ ዝብጠተ ፡ ማሕመሚ ፡ ወእመሰ ፡ ኮነ ፡ እምእንስሳ ፡ ይምትሩ ፡ እደዊሆሙ ። ወእለሂ ፡ ይሰርቁ ፡ እምሀገር ፡ ፩ደ ፡ ጊዜ ፡ እመ ፡ ኮኑ ፡ አብዕልተ ፡ ወአማዕዝያን ፡ ይፈድዩ ፡ ካዕበተ ፡ ለእግዚአ ፡ ንዋዩ ፡ እመሰ ፡ ኮኑ ፡ ነዳያን ፡ ይዝብጥዎሙ ፡ ወይሰድድዎሙ ፡ እመሰ ፡ ደገሙ ፡ ሰሪቀ ፡ ይምትሩ ፡ እደዊሆሙ ።

፩ሺ፯፻፺፮ መጽ ፡ ፻፲ወ፰ቱ ፡ ወሰረቅተ ፡ ሌሊትኒ ፡ እለ ፡ ይመጽኡ ፡ ኀበ ፡ ቤት ፡ ምስለ ፡ ንዋየ ፡ ሐቅል ። ወሰረቅተ ፡ መዓልትኒ ፡ መደንግፃን ፡ ወእለ ፡ ይፈትሑ ፡ አሕባለ ፡ ወእለ ፡ ይሰብሩ ፡ ቍልፋተ ፡ ይትገሠጹ ፡ እምአዘማዲሆሙ ፡ ወይፈድዩ ፡ ንዋየ ።

፩ሺ፯፻፺፯ ዘ፻፳ወ፪ቱ ፡ ወእለ ፡ ይከርዩ ፡ አብያተ ፡ እስመ ፡ ሕግነ ፡ ትኤዝዝ ፡ ከመ ፡ ኢንዕሊሆሙ ፡ እመሂ ፡ በሞት ፡ አው ፡ በተሰዶ ፡ አው ፡ በንሚእ ፡ ንዋዩ ።

፩ሺ፯፻፺፰ ራብዕ ፡ መጽ ፡ ፳ወ፩ዱ ፡ ወዘአስሐቶ ፡ ወሠጠ ፡ ለገብር ፡ ዘኢኮነ ፡ ሎቱ ፡ ወሰወሮ ፡ ያግብእ ፡ ኀበ ፡ እግዚኡ ፡ አው ፡ ሢጠ ፡ ዚአሁ ፡ አው ፡ አምሳሊሁኒ ።

፩ሺ፯፻፺፱ ጠስ ፡ ፴ወ፱ቱ ፡ ወእግዚአ ፡ ገብር ፡ ሰራቂ ፡ ይፈዲ ፡ ዘሰረቀ ፡ በዘሰከየ ፡ በእንቲአሁ ። ወለእመ ፡ ኢፈቀደ ፡ ያግብእ ፡ ሎቱ ፡ ገብረ ፡ ዚአሁ ፡ ለዘተሰርቀ ፡ ንዋዩ ፡ ይኩኖ ፡ ገብረ ፡ ለዓለሙ ። ወዘሂ ፡ ተመጠወ ፡ እምእደ ፡ ገብር ፡ ምንተኒ ፡ ዘተሰርቀ ፡ ያግብእ ፡ ኪያሁ ፡ ወ፬ተ ፡ እደ ፡ ምክዕቢተ ። ወዘንሥአ ፡ ገብረ ፡ ጕያዩ ፡ እምእግዚኡ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ያግብእ ፡ ኪያሁ ፡ ወካልአኒ ፡ ዘከማሁ ፡ አው ፡ ፳ ፡ ዲናረ ።

፩ሺ፰፻ ወዘሂ ፡ የሀይድ ፡ ንዋየ ፡ በጊዜ ፡ ውዕየተ ፡

ስለ ፡ ሌቦች ፡ ቅጣት ።

፩ሺ፯፻፺፬ ጠስ ፡ ፴፱ ። የእነርሱ ፡ ያልሆነውን ፡ መንጋ የሚነዱትን ፡ ሰዎች ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ይግረፋዋቸው ። በሁለተኛውም ፡ ጊዜ ፡ ያባርሯቸው ። በሦስተኛው ፡ እጃቸውን ፡ ይቁረጡዋቸው ፡ መንጋውም ፡ ወደጌታው ፡ ይመለስ ።

፩ሺ፯፻፺፭ ፫ኛ ፡ ጠስ ፡ ፴፱ ። ነፍስ ፡ ገዳይ ፡ የሆነ ፡ የሽፍቶች ፡ አለቃ ፡ እጁ ፡ ትቈረጥ ። የሚረዱትም ፡ ሰዎች ፡ እጆች ። ከከተማ ፡ የሚሰርቁ ፡ ሰዎች ፡ የሰረቁት ፡ ከጦር ፡ መሣሪያ ፡ ወገን ፡ ብቻ ፡ ቢሆን ፡ ጽኑ ፡ ግርፋት ፡ ይግረፏቸው ። ከእንስሳ ፡ ወገን ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ እጃቸውን ፡ ይቍረጡቸው ። ከሀገርም ፡ (ከገጠርም) ፡ ፩ ፡ ጊዜ ፡ የሰረቁ ፡ ሰዎች ፡ ባለጸጎችና ፡ ራሳቸውን ፡ የቻሉ ፡ ቢሆኑ ፡ ለባለ ፡ ገንዘቡ ፡ በእጠፌታ ፡ ይክፈሉ ፡ ድሆች ፡ ቢሆኑ ፡ ግን ፡ ገርፈው ፡ ይስደዷቸው ። ደግመው ፡ ቢሰርቁ ፡ ግን ፡ እጃቸውን ፡ ይቍረጡቸው ።

፩ሺ፯፻፺፮ መጽ ፡ ፻፲፰ ። የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ይዘው ፡ ወደቤት ፡ የሚመጡ ፡ የሌሊት ፡ ሌቦችም ፡ ሞት ፡ ይገባቸዋል ። የሚያስደነግጡ ፡ የቀን ፡ ሌቦችም ፡ ልባብ ፡ የሚያወልቁ ፡ ቁልፍም ፡ የሚሰብሩ ፡ በዘመዶቻቸው ፡ ይመከሩ ። ገንዘቡንም ፡ ይክፈሉ ።

፩ሺ፯፻፺፯ ፻፳፪ ። ቤት ፡ የሚምሱ ፡ ሰዎችም ፡ በሞት ፡ ወይም ፡ በስደት ፡ ወይም ፡ ገንዘብ ፡ በመክፈልም ቢሆን ፡ ሕጋችን ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ቅጣትን ፡ ታዝዛለች ፡ እኮን ።

፩ሺ፯፻፺፰ ፬ኛ ፡ መጽ ። ገንዘቡ ፡ ያልሆነውን ፡ ባሪያ ፡ አባብሎ ፡ የሸጠው ፡ የደበቀውም ፡ ወደ ጌታው ፡ ይመልሰው ። ወይም ፡ ዋጋውን ፡ ወይም ፡ መሰሉን ፡ ይመልስ ።

፩ሺ፯፻፺፱ ጠስ ፡ ፴፱ ። የሌባ ፡ ባሪያ ፡ ጌታ ፡ በተከሰሰበት ፡ የሰረቀውን ፡ ስለእርሱ ፡ ይክፈል ። (ሊከፍል) ፡ ባይወድም ፡ ለዘለዓለም ፡ ባሪያ ፡ ይሆነው ፡ ዘንድ ፡ የራሱን ፡ ባሪያ ፡ ገንዘቡ ፡ ለተሰረቀበት ፡ ሰው ፡ ይስጠው ። የተሰረቀውን ፡ ገንዘብ ፡ ማናቸውንም ፡ ከባሪያው ፡ እጅ ፡ የተቀበለ ፡ በይኑቱን ፡ ፬ ፡ ዕፅፍ ፡ አድርጎ ፡ ይክፈል ። ከጌታው ፡ የኮበለለውን ፡ ባሪያ ፡ የተቀበለ ፡ ሰው ፡ እርሱን ፡ ሌላም ፡ እንደርሱ ፡ ያለ፡ ወይም ፡ ኻያ ፡ ዲናር ፡ ይመልስ ፡ ዘንድ ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ፰፻ በእሳት ፡ ቃጠሎ ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ከፈረሰ ፡ ቤት ፡

አንቀጽ ፡ ፶ ።

እሳት ፡ አው ፡ እምነ ፡ ዘወድቀ ፡ ቤት ፡ አው ፡ እምነ ፡ ተሠጥመት ፡ ባሕር ፡ ወእለሂ ፡ ይትማጠዉ ፡ ዘንተ ፡ እምነገኢሁ ፡ በትሕሉት ፡ ይደልዎሙ ፡ ይፍድዩ ፡ ፬ተ ፡ እደ ፡ ለዘሂደዎ ፡ እስከ ፡ ዕደ፡ሚ፡ ዓመት ፡ ወለእመ ፡ ተዐደወ ፡ እምዓመት ፡ ይኩን ፡ ምክዕቢተ ።

፩ሺ፯፻፸፩ ወዘሂ ፡ ተማየጠ ፡ ግብረ ፡ ግዑዝ ፡ እንዘ ፡ የአምር ፡ ወሤጦ ፡ አው ፡ ወሀቦ ፡ ለካልእ ፡ አው ፡ ለትልወተ ፡ እንስት ፡ አው ፡ ለጸባሕት ፡ ወእም ፡ ከመ ፡ ተከሥተ ፡ በላዕሌሁ ፡ ፩ዱ ፡ እምእሉ ፡ ግብራት ፡ ይምትሩ ፡ እዴሁ ።

፩ሺ፯፻፸፪ ኀምስ ፡ ወእለሂ ፡ ይነሥኡ ፡ አልባሰ ፡ ምዉ ታን ፡ እምውስተ ፡ መቃብሪሆሙ ፡ ይምትሩ ፡ እደዊሆሙ ፡ ወባሕቱ ፡ ከልአ ፡ ሕግ ፡ መቲረ ፡ ፪ቱ ፡ አእዳው ፡ ወእገር ፡ ኅቡረ ።

፩ሺ፯፻፸፫ ወዳግማዊኒ ፡ መንፈሳዊ ፡ ረሰጠጅ ፡ ዘ፰ወ፫ቱ፡ ረሰጠብ ፡ ፶ ፡ እመቦ ፡ ካህን ፡ አው ፡ ሕዝባዊ ፡ ዘሰረቀ ፡ እምቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅብእ ፡ አው ፡ ስምእ ፡ ይሰደድ ፡ ወያግብእ ፡ ዘነሥአ ፡ ፭ተ ፡ እደ ፡ ምክዕቢተ ።

ስለ ፡ ስካርና ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ኃጢአቶች ።

ወይም ፡ በባሕር ፡ መስጠም ፡ ጊዜ ፡ ገንዘብ ፡ የሚቀማ ፡ ከነጣቂውም ፡ ይሁን ፡ በተንኮል ፡ የሚቀበሉ ፡ ሰዎች ፡ የተቀበሉትን ፡ ገንዘብ ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ አራት ፡ ዕጥፍ ፡ አድርገው ፡ ሊከፍሉ ፡ ይገባቸዋል ። ከአንድ ፡ ዓመትም ፡ ቢያልፍ ፡ ስምንት ፡ ዕጥፍ ፡ ይሁን ።

፩ሺ፯፻፸፩ ነፃ ፡ የወጣውን ፡ ባሪያ ፡ እያወቀ ፡ የገዛ ፡ የሸጠውም ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ለሴቶች ፡ ትልወት ፡ ወይም ፡ ለግብር ፡ አሳልፎ፡ የሰጠ ፡ ከእነዚህ ፡ ሥራዎች ፡ አንዱ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ከተገለጸ ፡ እጁን ፡ ይቈረጡት ።

፩ሺ፯፻፸፪ እምስተኛ ፡ ከመቃብራቸው ፡ ውስጥ ፡ አው ጥተው ፡ የሙታንን ፡ ልብስ ፡ የሚወስዱ ፡ ሰዎች ፡ እጆቻቸውን ፡ ይቈረጡ ። ነገር ፡ ግን ፡ ፪ ፡ እጅንና ፡ ፪ ፡ እግርን ፡ በአንድነት ፡ መቊረ ጥን ፡ ሕግ ፡ ከልክሏል ።

፩ሺ፯፻፸፫ ሁለተኛው ፡ መንፈሳዊ ፡ ነው ። ረሰጠጅ ፡ ፹፱ ፡ ረሰጠብ ፡ ፶ ። ካህን ፡ ወይም ፡ ሕዝባዊ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘይት ፡ ወይም ፡ ሰም ፡ የሰረቀ ፡ ቢኖር ፡ ይለይ ፡ የወሰደውንም ፡ እም ስት ፡ ዕጥፍ፡ አድርጎ ፡ ይመልስ ።

## አንቀጽ ፡ ፶ ፡

በእንተ ፡ ስካር ፡ ወርደ ፡ ወወልድ ፡ ዐላዊ ፡ ወበእንተ ፡ ውዱት ፡ ውኑ ሊቁ ፡ ኃጣውእ ።

፩ሺ፯፻፸፬ ቀዳሚ ፡ በእንተ ፡ ስከር ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ በወንጌል ፡ "ዑቁ ፡ ወተዓቀቡ ፡ እምስካር" ፡ ወይቤ ፡ ከመ ፡ ይትኳንን ፡ ዘይበልዕ ፡ ወይሰቲ ፡ ምስለ ፡ ስካርያን ፡ ነበ ፡ ሀሎ ፡ ብካይ ፡ ወሐቅየ ፡ ስነን ። ወጳውሎስኒ ፡ በውስተ ፡ መልእክቱ ፡ ለሰብእ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ይቤ ፡ "ከመ ፡ ኵሎሙ ፡ ስካርያን ፡ ወተዛልያን ፡ ወዘማውያን ፡ እሙ ንቱ ፡ ኢይወርስዋ ፡ ለመንግሥቱ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ወካልእ ፡ እምትድምርቶሙ ፡ ወእም በሊዕ ፡ ምስሌሆሙ ። ወኢሳይያስኒ ፡ ነቢይ ፡ ይሁቦሙ ፡ ወይሌ ፡ ለስካርያን ፡ ወይቤ ፡ "አሌ ፡ ሎሙ ፡ ለእለ ፡ ይገይሱ ፡ ወየሐውሩ ፡ ነበ ፡ ሰቴ ፡ ዘያሰክር ፡ ወይነብሩ ፡ ለስትየ ፡ ወይን ፡ በተው ኔት ፡ ወበማኅሌት ፡ እስከ ፡ ይመሲ ። ወሰሎሞ ንኒ ፡ ጠቢብ ፡ ወሀበ ፡ ወይሌ ፡ ውኁዘነ ፡ ወመቅ

## አንቀጽ ፡ ፶ ፡

ስለ ፡ ስካር ፡ ስለእራጣ ፡ ስለ ፡ ዐመፀኛ ፡ ልጅም፡ ስለ ፡ ነገር ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ ኃጢአትም ፡ ቍጥር ፡ ይናገራል ።

፩ሺ፯፻፸፬ መጀመሪያ፡ ስለስካር ፡ ይናገራል ። ጌታችን ፡ በወንጌል ፡ ከስካር ፡ እንድትጠበቁ ፡ ዕወቁ ፡ አለ ። (ሉቃ ፡ ፳፩ ፡ ፴፬) ፡ ከሰካራሞች ፡ ጋራ ፡ የሚበላና የሚጠጣ ፡ ሰውም ፡ ልቅሶ ፡ ጥርስ ፡ ማፋጨት ፡ ባለበት ፡ እንዲቀጣ ፡ ተናገረ ። (ማቴ ፡ ፳፬ ፡ ፵፺ - ፶፩) ። ጳውሎስም ፡ ለቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ በጻፈው ፡ መልእክቱ ፡ ሰካራሞች ፡ ነፍሰ ፡ ገዳ ዮች፡ አመንዝራዎች ፡ እሊህ፡ ሁሉ፡ የእግዚአብ ሔርን፡ መንግሥት፡ እንዳይወርሱ ፡ ተናገረ ። ከአ ንድነታቸውና ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ከመብላትም ፡ ከለከለ ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፲) ። ነቢዩ ፡ ኢሳይያ ስም ፡ ወደሚያሰክር ፡ መጠጥ ፡ ገሥግሠዉ ፡ የሚሔዱ ፡ በዘፈንና ፡ በሙዚቃ ፡ ወይን ፡ ለመ ጠጣት ፡ እስኪመሽ ፡ ድረስ ፡ የሚቀመጡ ፡ ወዮ ላቸው ፡ ብሎ ፡ ለሰካራሞች ፡ ልቅሶን ፡ ሰጥቷቸ

ሥፍት ፡ ወኵሎ ፡ ምንዳቤያቲ ፡ ለእለ ፡ ያዘ ልፉ ፡ ስክረ ፡ ወይቤ ፡ "ኢትኩን ፡ ሰኩሬ ፡ እስመ ፡ አንተ ፡ ለእመ ፡ አውተርከ ፡ ዓይንከ ፡ ኀበ ፡ እስተሐይጽ ፡ ጽዋዓት ፡ ወፍያላት ፡ ተሐውር ፡ ዕራቀከ ፡ እስመ ፡ ይነሬታ ፡ ለስካር ፡ የአኪ ፡ እምንስከተ ፡ ከይሲ" ። ወይቤ ፡ እስመ ፡ ስካር ፡ ይፈነውከ ፡ ኀበ ፡ ዝሙት ፡ ወዝሙትኒ ፡ ይወስደከ ፡ ኀበ ፡ ኀጕሉ ።

፩ሺ፯፻፸፮ ወናሁ ፡ ዘከሩ ፡ በአንቀጺ ፡ ካህናት ፡ ከመ ፡ ይደሉ ፡ በእንቲአሁ ፡ ተማግጸ ፡ ነቦኔ ፡ መንፈሳዊ ። ወዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ሰመዮ ፡ ለስካር ፡ ዕበደ ፡ ፈቃዳዌ ፡ ወእዝልፎ ፡ ስካር ፡ ይከውን ፡ ፍናተ ፡ ለኵሉ ፡ ምክንያተ ፡ ኃጢአት ፡ ወምንናት ። ወአዝልፎተ ፡ ስካርሰ ፡ በከመ ፡ ተነግረ ፡ ውስተ ፡ መጻሕፍት ፡ ጠቢባን ፡ ያመጽእ ፡ ነቀዮቀጠ ፡ ወጥፍአተ ፡ ልብ ፡ ወኀብስ ፡ ወሞተ ፡ ግብት ፡ ወረስንተ ፡ ወውስ የተ ፡ ወቍስለ ፡ አማሁት ፡ ወሕበጠ ፡ ናላ ፡ ወስእንተ ፡ ነቢብ ፡ ወወዲቀ ፡ አመካን ፡ ልዑል ፡ ውተወርዎ ፡ ውስተ ፡ ዓዘቅት ፡ ዕሙቅ ፡ ወውስተ ፡ መካን ፡ ክሩይ ፡

፩ሺ፯፻፸፯ ወሰትየ ፡ ወይንሰ ፡ በኀዳጥ ፡ በምክንያተ ፡ ፈውስ ፡ ናሁ ፡ አዘዞ ፡ ጳውሎስ ፡ ለጢሞቴዎስ ፡ ረድኡ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ "ንዳጠ ፡ ወይነ ፡ ቶስሕ በእንተ ፡ ደዌከ ፡ ዘዘልፍ" ።

፩ሺ፯፻፸፰ ወበተናግሮቶሙ ፡ ይቤሉ ፡ ሐዋርያት ፡ ረስጣ ፡ ፸ ፡ ኀየል ፡ ወመዐትም ፡ ኢይስተዩ ፡ ወይነ ፡ ከመ ፡ ኢይርስዕዎ ፡ ለጥበብ ፡ ወኢይትከሀሉ ፡ ከመ ፡ ይፍታሕ ፡ በርትዕ ። ወዘንቤሰ ፡ ዘንተ ፡ አኮ ፡ ንሕነ ፡ ዘንከልአሙ ፡ ከመ ፡ ኢይስተዩ ፡ ወይነ ፡ ለግሙራ ፡ እስመ ፡ ኢንክል ፡ ከመ ፡ ንመንን ፡ ዘፈጠረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለትፍሥሕተ ፡ ሰብእ ፡ እላ ፡ ንቤ ፡ ከመ ፡ ኢይስተዩ ፡ ብዙኀ ፡ ወኢይስክሩ ። እስመ ፡ ኢይቤሉ ፡ መጻሕፍት ፡ ኢይስተዩ ፡ ወይነ ፡ አላ ፡ ይቤሉ ፡ ኢይስተዩ ፡ ወይነ ፡ ለስካር ፡ ወዘንተ ፡ ንቤሎሙ ፡ ለካህናት ፡ ወለመሃይምናን ፡ ኅቡረ ።

፩ሺ፯፻፸፱ ዳግም ፡ በእንተ ፡ ርጾ ። በሕግ ፡ ተዳምሞ ፡ ከልአ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምንግሊ ፡ ርጾ ፡ ወዘ ሕግስ ፡ ዳግማዊ ፡ አዘዘ ፡ ከመ ፡ ይስትሕ ፡ ወኢ

ስለ ፡ ስካርና ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ኃጢአቶች ።

ዋል ። (ኢሳ ፡ ፭ ፡ ፲፩ - ፲፫) ። ብልሁ ፡ ሰሎሞንም ፡ ልቅሶና ፡ ኀዘንን ፡ መቅሠፍትን ፡ መከራዎችንም ፡ ሁሉ ፡ ስካርን ፡ ለሚያዘወትሩ ፡ ሰጠ። እንዲህም ፡ አለ ፡ ሰካራም ፡ አትሁን ። ጽዋዎችንና ኩባያዎችን ፡ ወደመመልከት ፡ ዓይንህን ፡ ብታዘወትር ፡ ዕራቁትህን ፡ ትሄዳለህና ። የስካር ፡ ፍጻሜዋ ፡ በእባብ ፡ ከመነከስ ፡ የሚከፋ ፡ ስለ ሆነ ። እንዲህም ፡ አለ ፡ ስካር ፡ ወደዝሙት ፡ ይወስድሀል ፡ ዝሙትም ፡ ወደጥፋት ፡ ይወስድሀል ፡ አኮ ። (ምሳ ፡ ፳፫ ፡ ፳፱ - ፴፭) ።

፩ሺ፯፻፸፮ በአንቀጹ ፡ ካህናትም ፡ ስለእርሱ ፡ መንፈሳዊ ፡ ቅጣት ፡ እንዲገባ ፡ እነሆ ፡ ተናገሩ ። (ፍ ፡ ነ ፡ ፲፱፻፳፬) ። ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅም ፡ ስካርን ፡ የፈቃድ ፡ ዕብደት ፡ ይለዋል ። ስካርን ፡ ማዘውተርም ፡ ለኃጢአትና ፡ ለተናቀው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ምክንያት ፡ ይሆናል ፡ ስካርን ፡ ማዘውተርስ ፡ በፈላስፎች ፡ መጽሐፍ ፡ እንደተነገረ ፡ መንቀጥቀጥን ፡ የልብ ፡ ጥፋትን ፡ ሳንባ ፡ በሽታን ፡ በድንገት ፡ መሞትን ፡ ተቅማጥን ፡ መቃጠልን ፡ የአንጀት ፡ ድርቀትን ፡ (ቍስልን) ፡ የናላ ፡ ማበጥን፡ ለመናገር ፡ አለመቻልን ፡ ከፍ ፡ ካለ ፡ ቦታ ፡ መውደቅን ፡ ከጥልቅ ፡ ጕድጓድና ፡ ከተቆፈረ ፡ ጕድጓድ ፡ መውደቅንም ፡ ያመጣል ።

፩ሺ፯፻፸፯ በደኅንነት ፡ ምክንያት ፡ በመጠኑ ፡ ወይን ፡ መጠጣትንስ ፡ እነሆ ፡ ጳውሎስ ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ጢሞቴዎስን ፡ ስለ ፡ ዘወትር ፡ ደዌህ ፡ ጥቂት ፡ ወይን ፡ ጨምር ፡ ብሎ ፡ አዝዞታል ። (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፭ ፡ ፳፫) ።

፩ሺ፯፻፸፰ ሐዋርያትም ፡ በመጻሕፍት ፡ እንዲህ ፡ አሉ ። ረስጣ ፡ ፸ ። ኀይለኛና ፡ ቁጡ ፡ ሰው ፡ ጥበብን ፡ እንዳይረሳት ፡ ወይን ፡ አይጠጣ ። በእውነትም ፡ ሊፈርድ ፡ አይቻለውምና ። ይህን ፡ ማለታችን ፡ ግን ፡ ፈጽመን ፡ ወይን ፡ ከመጠጣት ፡ እኛ ፡ የምንከለክላቸው ፡ አይደለንም ። እግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ሊደሰትበት ፡ የፈጠረውን ፡ ልንንቅ ፡ አንችልምና ። ብዙ ፡ እንዳይጠጡና ፡ እንዳይሰክሩ ፡ ተናገርን ፡ እንጂ ። መጻሕፍት ፡ ለስካር ፡ ወይን ፡ አይጠጡ ፡ አሉ ፡ እንጂ ፡ ወይን ፡ አይጠጡ ፡ አላሉምና ። ይህንም ፡ ለካህናትና ፡ ለምእመናን ፡ በአንድነት ፡ እንነግራቸዋለን ።

፩ሺ፯፻፸፱ ሁለተኛው ፡ ስለእራጣ ፡ ይናገራል ። እግዚአብሔር ፡ በመጀመሪያው ፡ ሕግ ፡ አራጣን ፡ ከለከለ ። (ዘፀ ፡ ፳፪ ፡ ፳፭) ። በሁለተኛው ፡ ሕግ፡

ይትረደዩ ። ወናሁ ፡ ተነግረ ፡ በቀኖናት ፡ ከመ ፡ ይኅድጉ ፡ ኪያሁ ፡ ወየሀቡ ፡ ንስሐ ፡ በእንቲአሁ ። ረስጠጅ ፡ ፵ወ ፪ቱ ፡ እመሰ ፡ እምካህናት ፡ ሀሎ ፡ ወሕዝባውያን ፡ ዘነሥአ ፡ ምንተኒ ፡ እምርዴ ፡ ለያኅድግ ፡ ወእመ ፡ አኮሰ ፡ ለያውግዝ ።

፩ሺ፯፻፸፱ ዘኒቅያ ፡ በተፍጻሜቱ ፡ ኢትኩን ፡ መአብሰ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሶበ ፡ ትፈቅድ ፡ ነሢአ ፡ ርዴ ፡ እምኔሁ ፡ ወለእመ ፡ ብከ ፡ ፋሬያት ፡ አው ፡ ወርቅ ፡ ወኢትፍቅድ ፡ ነሢአ ፡ ርዴ ፡ እምኔሁ ፡ ወሚጥከ ፡ በብዙኅ ፡ ሤጥ ፡ ትከውን ፡ ምኑነ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ እስመ ፡ አንተ ፡ ህየንተ ፡ ነሢአ ፡ ርዴ ፡ ነሣእከ ፡ ፫ተ ፡ አው ፡ ፬ተ ፡ እደ ፡ ካዕበተ ፡ ርዴ ።

፩ሺ፯፻፹ ፲ወ፯ቱ ፡ ወብዙኃን ፡ እለ ፡ ያፈቅሩ ፡ ለነሢአ ፡ ክፍል ፡ ዐቢይ ፡ ወረስዑ ፡ ቃለ ፡ ቅዱስ ፡ ዘይቤ ፡ "ወዘኢለቅሐ ፡ ወርቆ ፡ በርዴ" ። ለእለሰ ፡ ይነሥኡ ፡ ርዴ ፡ ይቤሎሙ ፡ ማኅበር ፡ ዐቢይ ፡ ለእመ ፡ ተረክበ ፡ ፩ዱ ፡ ዘይነሥእ ፡ ርዴ ፡ አው ፡ ዘይገብር ፡ ካልአ ፡ ግብረ ፡ ዘከመዝ ፡ አው ፡ ዘይሌቅሕ ፡ ሥርናዮ ፡ በርዴ ፡ አው ፡ ዘይትመከነይ ፡ ቦቱ ፡ ተመከንዮተ ፡ በእንተ ፡ ነሢአ ፡ ረባኅ ፡ ርኩስ ፡ ይትመተር ፡ ወይረስይዎ ፡ ነኪረ ።

፩ሺ፯፻፹፩ ሣልስ ፡ በእንተ ፡ ወልድ ፡ ዐላዊ ፡ መጽ ፡ ፩ቱ ፡ ይሰድድዎ ፡ ለወልድ ፡ ዐላዊ ፡ እማእከለ ፡ ጉባኤ ፡ ወይሣኤ ፡ እምርስቱ ፡ ወላድያኒሁ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አዘዘ ፡ በውስተ ፡ ብሉይ ፡ ቀትለ ፡ ዚአሁ ፡ በውግረተ ፡ እብን ። ወሕግሰ ፡ ወሚሓዊት ፡ ተራኅርኀት ፡ ላዕሌሁ ፡ ወአዘዘት ፡ በዝንቱ ፡ ውሳኔ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ወልድ ፡ ዐላዌ ፡ ወዘየሐሥም ፡ ላዕለ ፡ ወላድያኒሁ ፡ ብዉሕ ፡ ሎሙ ፡ ከመ ፡ ይሰድድዎ ፡ ሎቱ ፡ ወይንግሩ ፡ በቅድመ ፡ መኳንንት ፡ ወጉባኤ ፡ ስደተ ፡ ዚአሁ ፡ እምወላድያኒሆሙ ፡ ወእምነ ፡ ርስቶሙ ።

፩ሺ፯፻፹፪ ራብዕ ፡ በእንተ ፡ ውዳሴ ። መክ ፡ ፻፲ወ፰ቱ ፡ እመሰ ፡ ዘያስተዋድዮ ፡ ለ፩ዱ ፡ በምንትኒ ፡ እምግብር ፡ ሕሡም ፡ ያቅም ፡ ተሐባዪ ፡ ከመ ፡ ው



ግን ፡ አበድረው ፡ እንዳይቀበሉ ፡ አዘዘ ። (ሉቃ ፡ ፮ ፡ ፴) ። በመጻሕፍትም ፡ እርሱን ፡ እንዲተዉ ፡ ስለእርሱም ፡ ንስሐ ፡ እንዲሰጣቸው ፡ እነሆ ፡ ተነገረ ። ረስጠጅ ፡ ፵፪ ። ከካህናትና ፡ ከሕዝባውያን ፡ ከአራጣ ፡ ወገን ፡ ምንም ፡ ምን ፡ የተቀበለ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ይተው ። ባይተው ፡ ግን ፡ ይሻር ።

፩ሺ፯፻፸፱ ኒቅያ ፡ በመጨረሻው ። ከወንድምህ ፡ አራጣ ፡ መቀበልን ፡ በወደድህ ፡ ጊዜ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በደለኛ ፡ አትሁን ። እህል ፡ ወይም ፡ ወርቅ ፡ ቢኖርህ ፡ ከእርሱ ፡ አራጣ ፡ መቀበልን ፡ አትውደድ ። በብዙ ፡ ዋጋ ፡ ብትሸጠውም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የተናቅህ ፡ ትሆናለህ ። አንተ ፡ አራጣ ፡ ስለመቀበል ፡ ፈንታ ፡ ፫ ፡ ወይም ፡ አራት ፡ እጅ ፡ የአራጣ ፡ አጠፌታ ፡ ወስደሃልና ።

፩ሺ፯፻፹ ፲፯ ። ክፍ ፡ ያለውን ፡ ክፍል ፡ ለመውሰድ ፡ የሚፋጠኑ ፡ ወርቁን ፡ በአራጣ ፡ ያላበደረ ፡ የሚለውን ፡ ቅዱስ ፡ ቃል ፡ የረሱ ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ። አራጣ ፡ የሚቀበሉትንስ ፡ ታላቁ ፡ ጉባኤ ፡ አራጣ ፡ የሚቀበል ፡ ወይም ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ስንዴውን ፡ በአራጣ ፡ የሚያበድር ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ርኩስ ፡ የሆነ ፡ ትርፍን ፡ ለማግኘት ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የሚያመካኝ ፡ ሰው ፡ ቢገኝ ፡ ይለይ ። እንደ ፡ ባዕድም ፡ ያድርጉት ፡ ብሏቸዋል ።

፩ሺ፯፻፹፩ ፫ኛ ፡ ስለወንጀለኛ ፡ (ዓመፀኛ) ፡ ልጅ ፡ ይናገራል ። መጽ ፡ ፩ ። ወንጀለኛውን ፡ (ዓመፀኛውን) ፡ ልጅ ፡ ከጉባኤ ፡ ይለዩት ። ከወላጆቹም ፡ ርስት ፡ ይነቀል ። እግዚአብሔር ፡ በኦሪት ፡ በደንጋይ ፡ ተወግሮ ፡ እንዲሞት ፡ አዝዞአልና ። (ዘፀ ፡ ፳፩ ፡ ፲፯) ። ዘዳ ፡ ፳፩ ፡ ፲፰ - ፳፩)። የክርስቶስ ፡ ሕግ ፡ ግን ፡ ለእርሱ ፡ ርኅራኄ ፡ አድርጋ ፡ ይህን ፡ ውሳኔ ፡ አዘዘች ። ልጅ ፡ ወንጀለኛ ፡ (ዓመፀኛ) ፡ ቢሆን ፡ በወላጆቹም ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ የሚሠራ ፡ ቢሆን ፡ ሊያባርሩት ፡ ይገባቸዋል ። ከወላጅነታቸውና ፡ ከርስታቸው ፡ መነቀሉን ፡ በዳኞችና ፡ በጉባኤ ፡ ፊት ፡ ይንገሩ ።

፩ሺ፯፻፹፪ ፬ኛ ። ስለ ፡ ነገር ፡ ሥራ ፡ ይናገራል ። መክ ፡ ፻፲፰ ። ከክፉ ፡ ሥራ ፡ ወገን ፡ በማናቸውም ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ ነገር ፡ የሚሠራ ፡ ቢኖር ፡ ምስክ

እሳት ፡ ያጸንዕ ፡ ቃሎ ፡ እሙነ ፡ በአትሞ ፡ ሰማዕት ፡ ወምእመናን ፡ እደው ፡ ለውእቱ ፡ ብእሲ ። ወለእመ ፡ ኢክሀለ ፡ ላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ ይፍዲ ፡ በአምሳነ ፡ ዘበነ ፡ ይፈድዮ ፡ ለቢጹ ፡ ዝኩ ፡ ብእሲ ፡ እመ ፡ ተጠየቀ ፡ በላዕሌሁ ፡ ዝንቱ ፡ ግብር ፡ ወከማሁ ፡ ይኩን ፡ ኵነኔሁ ።

፩ሺ፯፻፹፫ ድስቅ ፡ ፲ቱ ፡ ወእምከመ ፡ ፈታሕክሙ ፡ ዘእንበለ ፡ አድልዎ ፡ ተአምሩ ፡ ሐሰተ ፡ ዚአሁ ፡ ለዘያስተዋድዮ ፡ ለቢጹ ፡ በከንቱ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ፍጡነ ፡ ይወድቅ ፡ በቃለ ፡ አፉሁ ፡ ወለዝንቱኒ ፡ መናፍቅ ፡ ከመ ፡ ይኩንንዎ ፡ ገሃደ ፡ ወይግበሩ ፡ ቦቱ ፡ በከመ ፡ ውእቱ ፡ ፈቀደ ፡ ይግበር ፡ ዲበ ፡ ቢጹ ። ወለዘሰ ፡ ዘይሔስ ፡ ዲበ ፡ ቢጹ ፡ ኢትንድግዎ ፡ ዘእንበለ ፡ ኵነኔ ፡ ከመ ፡ ኢይትኀበል ፡ ላዕለ ፡ ነገር ፡ ከንቱ ፡ በዘይሔውር ፡ በፍኖት ፡ ርትዕት ፡ አው ፡ ከመ ፡ ኢይትኀበል ፡ ካልእ ፡ ወኢይግበር ፡ በከመ ፡ ምግባሩ ፡ ወኢያድልዎ ፡ ለእኩይ ፡ ከመ ፡ ይከሥት ፡ ዓቢየ ፡ አበሳ ፡ እኩየ ፡ ወእመ ፡ አኮሰ ፡ ኢይስምዖ ፡ እምኔሁ ፡ ወይንበር ፡ በስደት ።

፩ሺ፯፻፹፬ ኃምስ ፡ በእንተ ፡ ሥራይ ። ጠስ ፡ ፵፰ቱ ፡ ዘየአምሮ ፡ ለገባሬ ፡ ሥራይ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ያግብኦ ፡ ለመስፍን ፡ ወለእመ ፡ ኀብአ ፡ ኢሐዲ ፡ ወኢያግብኦ ፡ ለመኰንን ፡ ይደልዎ ፡ ለሊሁ ፡ ሥቃይ ፡ ዕፁብ ። ወእለ ፡ ይገብሩ ፡ እልሐዘረ ፡ በኮርናዕ ፡ ወይፈቅዱ ፡ ቦቱ ፡ ይርብሑ ፡ ረባሐ ፡ በውእቱ ፡ ረቢሖት ፡ ፍትር ፡ ይዘበጡ ፡ ወይሰደዱ ።

፩ሺ፯፻፹፭ ሳድስ ፡ በእንተ ፡ ውዕየት ፡ ዘንገሥት ፡ ፳ወ፬ቱ ፡ ወዘወደየ ፡ እሳተ ፡ ውስተ ፡ ሀገር ፡ አው ፡ በሐቅል ፡ እንዘ ፡ የኀሥሥ ፡ ንክየተ ፡ ሰብእ ፡ ዘኢኮነ ፡ ለየዐይ ።

፩ሺ፯፻፹፮ ጠስ ፡ ፵፰ቱ ፡ ለእመ ፡ ተዐውቀ ፡ ፩ዱ ፡ ከመ ፡ አውዐየ ፡ ማኅደረ ፡ በእሳት ፡ በእእምሮቱ ፡ ወበፈቃዱ ፡ ይትኰነን ፡

፩ሺ፯፻፹፯ ወለእመ ፡ አውዐየ ፡ ፩ደ ፡ ዓፀደ ፡ በእኀብሮ ፡ ወወዕአ ፡ እሳት ፡ ወአውዐየ ፡ እብያተ ፡ ዘዓውዱ ፡ አልቦ ፡ ዕዳ ፡ ላዕለ ፡ ዘአውዐየ ፡ ቀዲሙ ።

፩ሺ፯፻፹፰ ወዘኒ ፡ ወደየ ፡ እሳተ ፡ ውስተ ፡ ገራህቱ ፡ ወሐረት ፡ እስከ ፡ አውዐየት ፡ ዘርእ ፡ ጎሩ ፡ ይሕትትዎ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘኢተዐቅበ ፡ በኵሉ ፡ ክሂሎቱ ፡ ከመ ፡ ኢይሑር ፡ እሳት ፡ ኀበ ፡ መካን



ሮችንና ፡ እውነተኞች ፡ ሰዎችን ፡ በመጥራት ፡ እውነተኛ ፡ ቃሉን ፡ እንደሚያጸና ፡ ዋስ ፡ ይጥራ ፡ በዚህ ፡ ባይችል ፡ ያ ፡ ሰው ፡ ለባልንጀራው ፡ ያከፍለው ፡ በነበረው ፡ ልክ ፡ ይከፈል ። ይህ ፡ ሥራ ፡ በእርሱ ፡ ቢረጋገጥ ፡ ቅጣቱም ፡ እንደዚሁ ፡ ይሁን ።

፩ሺ፯፻፹፫ ድስቅ ፡ ፲ ። ያለአድልዎ ፡ ከፈረዳችሁ ፡ ባልጀራውን ፡ በከንቱ ፡ የሚከሰውን ፡ ሰው ፡ ሐሰት ፡ ታውቃላችሁ ። እርሱ ፡ በአነጋገሩ ፡ ፈጥኖ ፡ ይወድቃልና ። ይህንም ፡ ሰው ፡ በግልጥ ፡ ሊፈርዱበት ፡ ይገባል ። በባልንጀራውም ፡ ሊያደርግበት ፡ የወደደውን ፡ በእርሱ ፡ ያድርጉበት ። በጓደኛውም ፡ ላይ ፡ ሐሰት ፡ የሚናገረውን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ያለ ፡ ቅጣት ፡ አትተዉት ። በቀናች ፡ መንገድ ፡ በሚሄደው ፡ ሰው ፡ በከንቱ ፡ ነገር ፡ እንዳይደፋፈር ፡ ወይም ፡ ሌላው ፡ እንዳይደፋፈር ፡ እንደ ፡ ሥራውም ፡ እንዳይሠራ ። ወንድም ፡ የወንድሙን ፡ ታላቅ ፡ በደል ፡ ሊገልጽ ፡ አይገባውም ። ያም ፡ ባይሆን ፡ ከእርሱ ፡ አይስሙ ። በስደትም ፡ ይኑር ።

፩ሺ፯፻፹፬ አምስተኛው ፡ ስለ ፡ ሥራይ ፡ ይናገራል ። ጠስ ፡ ፵፰ ። ሥራይ ፡ አድራጊውን ፡ የሚያውቀው ፡ ሰው ፡ ለዳኛ ፡ ሊያቀርበው ፡ ይገባዋል ። አንድ ፡ ሰውም ፡ ደብቆ ፡ ባያቀርበው ፡ ጭንቅ ፡ ቅጣት ፡ ይገባዋል ። መንድግ ፡ በክንድ ፡ የሚያደርጉ ፡ በዚህም ፡ መስተፋቅር ፡ ጥቅምን ፡ ሊጠቀሙበት ፡ የሚወዱ ፡ ተገርፈው ፡ ይሰደዱ ።

፩ሺ፯፻፹፭ ስድስተኛ ፡ ስለቃጠሎ ፡ ይናገራል ። ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ፳፬ ። የመንደሮችን ፡ ሰዎች ፡ ጉዳት ፡ ሽቶ ፡ በሀገር ፡ ወይም ፡ በዱር ፡ እሳት ፡ የጨመረ ፡ ሰው ፡ ይቃጠል ።

፩ሺ፯፻፹፮ ጠስ ፡ ፵፰ ። አንድ ፡ ሰው ፡ ዐውቆ ፡ በፈቃዱ ፡ ቤት ፡ እንዳቃጠለ ፡ ቢታወቅ ፡ ይቀጣ ።

፩ሺ፯፻፹፯ በመተባበር ፡ አንድ ፡ ቦታ ፡ ቢያቃጥል ፡ እሳትም ፡ ወጥቶ ፡ በዙሪያው ፡ ያለውን ፡ መንደር ፡ ቢያቃጥል ፡ መጀመሪያ ፡ ባያየዘው ፡ ዕዳ ፡ የለበትም ።

፩ሺ፯፻፹፰ በእርሻው ፡ ላይ ፡ እሳት ፡ ያቀጣጠለ ፡ ሰው ፡ የጎረቤቱንም ፡ እዝመራ ፡ እስከታቃጥል ፡ ድረስ ፡ ብትሄድ ፡ እሳት ፡ ወደሌላው ፡ ቦታ ፡ እንዳይተላለፍ ፡ በተቻለው ፡ ሁሉ ፡ ያልተጠነ

አንቀጽ ፡ ፶ ።

ካልእ ፡ ወይፍትሑ ፡ ላዕሌሁ ፡ ፍትሐ ፡ ሀካይ ያን ፡ ወእመሰ ፡ ኮነ ፡ ዘይትሀቀብ ፡ በኵሉ ፡ ግብር ፡ ሶበ ፡ ኀየሎ ፡ ነፍስ ፡ ወነፍሐ ፡ ለእሳት ፡ እልቦ ፡ ስዳ ፡ ላዕለ ፡ አንዳዪ ፡ እሳት ፡

፩ሺ.፯፻፹፱ ሳብሰ ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡ ኊልቈ ፡ አበሳት ። ጠስ ፡ ፴ወ፰፡ ፡ ወሰእመ ፡ ውስየ ፡ ሥጋ ፡ አማ ዓዚ ፡ ይደልዎ ፡ ለፈታሒ ፡ ከመ ፡ ይፍታሕ ፡ ላዕለ ፡ ገባሪ ፡ በእንተ ፡ ፈውሳት ፡ ወሥራሓት ፡ ወበእንተ ፡ ሕጸጸ ፡ መልክዕሰ ፡ አልቦ ፡ እስመ ፡ ሥጋሁሰ ፡ ለእግዓዚ ፡ ኢይትሜጠን ፡ በሤጥ ። ወዘእውፀየሰ ፡ እምሥጋ ፡ ገብር ፡ ይደልዎ ፡ ተኀሥሦ ፡ በዘእቅደምነ ፡ ዘክሮ ፡ በዘየሐጽጽ እምሤጡ ።

፩ሺ.፯፻፺ ዘ፴ወ፱፡ ፡ ወዘሂ ፡ ይሞቅሕ ፡ እንስሳ ፡ ዘሐ ኮነ ፡ ሎቱ ፡ ወይቀትሎ ፡ በኀጢእ ፡ መባልዕት ፡ እው ፡ በካልእ ፡ ፍና ፡ ይደልዎ ፡ ፈድየ ፡ ካስ በት ፡ ሎቱ ።

፩ሺ.፯፻፺፩ ወዘይትዔገል ፡ ምድረ ፡ አው ፡ ዘየፈልስ ፡ ደወለ ፡ ይደልዎ ፡ ያግብእ ፡ ካዕበቶ ፡ ለዘነሥአ ።

፩ሺ.፯፻፺፪ ወመሐዛትኒ ፡ እለ ፡ የሀውኩ ፡ ጉባኤ ፡ እመ ፡ ሊቀ ፡ ሀገር ፡ ኮነ ፡ ነገሮሙ ፡ ወነበሩ ፡ ውስተ ፡ ስሕተቶሙ ፡ ይደልዎሙ ፡ ስደት ። ወለእመሰ ፡ ኮነንዎሙ ፡ ብዙኀ ፡ ጊዜያተ ፡ ወቆሙ ፡ ዳግመ፡ ውስተ ፡ ድፍረቶሙ ፡ ይዝብጥዎሙ ፡ ወይላጽዩ ርእሶሙ ፡ ወያዝልፉ ፡ ነቢረ ፡ ውስተ ፡ ስደት ፡ ወእመሰ ፡ ኮነ ፡ ሊቀ ፡ ዘኢአመሮሙ ፡ ይዝብጥ ዎሙ ፡ በበትር ፡ ባሕቲቱ ፡ ወይኅድግዎሙ ።

፩ሺ.፯፻፺፫ ወዘሂ ፡ ይገብር ፡ ማኅተመ ፡ በዲናራት ፡ ይምትሩ ፡ እደዊሁ ።

፩ሺ.፯፻፺፬ ሳምን ፡ መጅ ፡ ፲ወ፱፡ ፡ ወዘሂ ፡ ተዐየወ ፡ ላዕለ ፡ ካህን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይዝብጥዎ ፡ ወይሰድድዎ ፡ ወዘሂ ፡ ተዐየወ ፡ ላዕለ ፡ ዘተማኅፀነ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወዘአውፅአ ፡ እምኔሁ ፡ በኀይል ፡ ይትቀሠፍ ፡ ፲ወ፪ተ ፡ ጊዜያተ ፡ ወይትአኀዝ ፡ በዘይደሉ ፡ በእንተ ፡ ጕያዪ፡ ዘተማኅፀነ ፡ ኀቤሃ ። ወባሕቱ ፡ ይትመጠውዎ ፡ ካህን ፡ ወሰብእ ፡ ፈራህያን ፡ እምእኩይ ፡ ሕዝብ ፡ ወይክሥቱ ፡ ምክንያተ ፡ ጕይዮቱ ፡ ወይፍትሑ ፡ ላዕሌሁ ፡ በከመ ፡ አዘዘ ፡ ሕግ ።

፩ሺ.፯፻፺፭ ሥርዋጽ ፡ ወከሓድያን ፡ ዘነዋ ፡ ይትረከቡ ፡

ስለ ፡ ስካርና ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ኃጢአቶች ።

ቀቀ ፡ ቢሆን ፡ ይመርምሩት ። በችልተኞችም ፡ ፍርድ ፡ ይፍረዱበት ። በሥራዉ ፡ ሁሉ ፡ የተጠበቀ ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ነፋስም ፡ እያሎ ፡ እሳቱን ፡ ቢያናድደው ፡ እሳቱን ፡ ባያያዘው ፡ ሰው ፡ ዕዳ ፡ የለበትም ።

፩ሺ.፯፻፹፱ ሰባተኛ ፡ ስለበደሎች ፡ ሁሉ ፡ ቍጥር ፡ ይናገራል ። ጠስ ፡ ፴፰ ። የጨዋ ፡ ልጅ ፡ አካል ፡ በእሳት ፡ ቢቃጠል ፡ ዳኛ ፡ በአድራጊው ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ መድኃኒትና ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ (ለመድኃኒት ፡ ስለከፈለውና ፡ ሥራ ፡ ስለፈታበት) ፡ ሊፈርድ ፡ ይገባዋል ። ስለ ፡ አካል ፡ ጉድለት ፡ ግን ፡ የለም ። የጨዋ ፡ ልጅ ፡ አካል ፡ በዋጋ ፡ አይገመትምና ። የባሪያ ፡ አካል ፡ ያቃጠለ ፡ ግን ፡ አስቀድመን ፡ እንደተናገርን ፡ ከዋጋው ፡ በሚጎድል ፡ መፈላለግ ፡ ይገባል ።

፩ሺ.፯፻፺ ፴፱ ። ገንዘቡ ፡ ያልሆነውን ፡ እንስሳ ፡ አሥሮ፡ ምግብ ፡ በመከልከል ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ የገደለው ፡ ለባለቤቱ ፡ ዕጥፍ ፡ አድርጎ ፡ መክፈል ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ.፯፻፺፩ ምድር ፡ የሚጋፋ ፡ ወይም ፡ ድንበር ፡ የሚያፈርስ ፡ የወሰደውን ፡ ስጥፍ ፡ አድርጎ ፡ ሊመልስ ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ.፯፻፺፪ ጉባኤን ፡ (ስብሰባን) ፡ የሚያውኩ ፡ ጎበዛዝትም ፡ አገር ፡ አሳዳሪዉ ፡ ነግሯቸው ፡ በስሕተታቸው ፡ ቢኖሩ ፡ ስደት ፡ ይገባቸዋል ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቀጥተዋቸው ፡ ዳግመኛ ፡ በድፍረታቸው ፡ ቢጸኑ ፡ ይግረፉቸው ። ራሳቸውንም ፡ ይላጯቸው ። በስደት ፡ መኖርንም ፡ ያዘውትሩ። ዳኛ ፡ ያላስጠነቀቃቸው ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ በበትር፡ ብቻ ፡ ደብድበው ፡ ይተዋቸው ።

፩ሺ.፯፻፺፫ በዲናር ፡ ማኅተም ፡ የሚሠራ ፡ እጁን ፡ ይቊረጡት ።

፩ሺ.፯፻፺፬ ስምንተኛ ፡ መጅ ፡ ፲፱ ። በቤተ ፡ ክርስቲያኑ፡ አገልጋይ ፡ ላይ ፡ የተደፋፈረውንም ፡ ይግረፉት ያባርሩትም ። በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተማፀነውንም ፡ ሰው ፡ ተደፋፍሮ ፡ በኀይል ፡ ከእርሱ ፡ ያወጣው ፡ ፲፪ ፡ ጊዜ ፡ ይገረፍ ። በእርሱዋ ፡ የተማፀነውም ፡ ስለከበለለ ፡ በሚገባ ፡ ይያዝ ። ነገር ግን ፡ ካህኑና ፡ ከሕዝቡ ፡ ሽማግሌዎች ፡ እግዚአብሔርን ፡ በሚፈሩ ፡ ሰዎች ፡ ተቀብለው ፡ የሸሸበትን ፡ (የደወለበትን) ፡ ምክንያት ፡ ይግለጡ። ሕግም ፡ እንደሚያገዘው ፡ ይፍረዱለት ።

፩ሺ.፯፻፺፭ ሥርዋጽ ። (ከወላጆች) ፡ ከሞታቸው ፡ በኋላ፡

ወእምድኅረ ፡ ፍልስቶሙ ፡ ኢያውርስዎሙ ፡ ለዕሩኒ ፡ ኢበጽሒፈ ፡ ትእዛዝ ፡ ወኢ ፡ ዘእንበለ ፡ ትእዛዝ ። ወለእመኒ ፡ ኮኑ ፡ እዝማዲሁ ፡ አርቶዶክሳውያን ፡ ዘእንበለ ፡ ባሕቲቱ ፡ ውሉዶሙ ፡ ለእመ ፡ ኮኑ ፡ አርቶዶክሳውያን ፡ እላ ፡ የሀቡ ፡ ንዋዮሙ ፡ ለንጉሥ ። ወእለሂ ፡ ይትፈለጡ ፡ እምሃይማኖት ፡ ኢይክውኖሙ ፡ ጽሒፈ ፡ ትእዛዝ ፡ ወኢ ፡ ከመ ፡ የሀቡ ፡ ኢ ፡ በትእዛዝ ፡ ወኢ ፡ ዘእንበለ ፡ ትእዛዝ ፡ ወኢይረሱ ፡ ምንተኒ።

የሚገኙ ፡ ከሐዲዎችም ፡ ለአንዱስ ፡ እንኳ ፡ በማዘዣ ፡ ደብዳቤ ፡ ወይም ፡ ያለ ፡ ትእዛዝ ፡ አያውርሱዋቸው ። ዘመዶቹ ፡ አርቶዶክሳውያን ፡ ቢሆኑም ፡ ልጆች ፡ ብቻ ፡ አርቶዶክሳውያን ፡ ካልሆኑ ፡ ገንዘባቸውን ፡ ለንጉሥ ፡ ይስጡ፡ እንጂ ። ከሃይማኖት ፡ የተለዩ ፡ ሰዎች ፡ ትእዛዝ መጻፍና ፡ በትእዛዝ ፡ ወይም ፡ ያለትእዛዝ ፡ ሊሰጡ ፡ አይገባቸውም ፡ እንዳችም ፡ አይውረሱ ።

## አንቀጽ ፡ ፶ወ፪ቱ ፡

በእንተ ፡ ሥዕርት ፡ ወግዝረት ፡ ወተእምኖ ፡ ወበእንተ ፡ ኵሉ ፡ ዘይደልዎ ፡ ለሊቅ ፡ ከመ ፡ ይወስክ ፡ ቦቱ ፡ ወያንትግ ፡ እምኔሁ ፡ በመዋዕሊሁ ፡ በከመ ፡ ይደሉ ፡ ለገቢር ፡ በትእዛዘ ፡ ቀኖናት ።

፩ሺ፯፻፺፩ ሥዕርትሰ ፡ ኢይደልዎሙ ፡ ለእደው ፡ ከመ ፡ ያንኁ ፡ ሥዕርቶሙ ፡ ወረድኣደስ ፡ ሐሢኖቱ ፡ ወፀፍሮቱ ፡ ወእምኵሉ ፡ ዘየዐቢ ፡ ለካህናት ፡ እላ ፡ ይደሉ ፡ ላዕሌሆሙ ። ወዘኢይደልዎ ፡ እንሶቱ ፡ ከመ ፡ ቃለ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ለሰብእ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ዘይቤ ፡ "ኢያሀውቀክሙኑ ፡ ፍጥረት ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ከመ ፡ ለእመ ፡ እንኳ ፡ ብእሲ ፡ ሥዕርተ ፡ ርእሱ ፡ ኀሣር ፡ ውእቱ ፡ ሎቱ" ። ወበእንተ ፡ ዘእዘዘ ፡ በእንቲአሁ ፡ ለጢሞቴዎስ ፡ ረድኡ ፡ ገሥጾተ ፡ አንስት ፡ ከመ ፡ ይትገኃሣ ፡ እምተሠርግዎ ፡ በተፀፍሮ ፡ ሥዕርት ። ወበእንተ ፡ ዘከልአን ፡ እምኔሁ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሐዋርያ ፡ ዘይቤ ፡ በብሂሎቱ፡ ኢትሠርገዋ ፡ በተፀፍሮ ፡ ሥዕርት ። ወለእመሰኬ ፡ ከልእዎን ፡ ለአንስት ፡ እምነ ፡ ዝንቱ ፡ ማ ፡ መጠን ፡ ይደልዎሙ ፡ ለእደው ፡ ተከልአ ፡ እምኔሁ ።

## አንቀጽ ፡ ፶፪ ።

ስለጠጉርና ፡ ስለግዝረት ፡ ስለ ፡ መታመን ፡ በመጻሕፍት ፡ ትእዛዝ ፡ ለመሥራት ፡ ለዳኛ ፡ በዘመኑ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ሊጨምር ፡ ከእርሱም ፡ ሊያጎድል ፡ ስለሚገባውም ፡ ሁሉ ፡ ይናገራል ።

፩ሺ፯፻፺፩ ስለ ፡ ፀጉርስ ፡ ለወንዶች ፡ ፀጉራቸውን ፡ ሊያሳድጉ ፡ አይገባቸውም ። ይልቁንም ፡ ማሳደጉና ፡ መሠራቱ ። ከሁሉም ፡ የሚበልጥ ፡ ለካህናት ፡ ሊላጩት ፡ ይገባል ፡ እንጂ ። ማሳደጉ ፡ አለመገባቱስ ፡ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ ለቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ እንደተናገረው ፡ ነው ። ወንድ ፡ ጠጉሩን ፡ ቢያሳድግ ፡ ለእርሱ ፡ ተዋርዶው ፡ እንደሆነ ፡ ስለዚህ ፡ ፍጥረት ፡ አያሳውቃችሁምን ? (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፲፫ - ፲፭).። ለደቀመዝሙሩ ፡ ለጢሞቴዎስም ፡ ስለእርሱ ፡ ጠጉራቸውን ፡ በመሠራት ፡ ከማጌጥ ፡ ይርቁ ፡ ዘንድ ፡ ሴቶችን ፡ ማስማተርን ፡ ስለአዘዘ ፡ ነው ። ( ፩ ፡ ጢሞ ፪ ፡ ፱ - ፲ ) ። ሐዋርያ ፡ ጴጥሮስም ፡ ጠጉራችሁን ፡ በመሠራት ፡ አታጊጡ ፡ በማለቱ፡ከእርሱ፡ስለከለከላቸው ፡ ነው ። (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፩ - ፮) ። ከዚህ፡ ሥራ ፡ ሴቶችን ፡ ከከለከሉአቸው ፡ ለወንዶችማ፡ ከዚህ ፡ ሥራ ፡ መከልከል ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ይገባቸው ፡ ይሆን !

፩ሺ፯፻፺፪ ወኢኀደግነ ፡ ዘከረተ ፡ እደው ፡ ምስለ ፡ አንስት ፡ በዝየ ፡ በእንተ ፡ ልማዶሙ ፡ በበይነ ፡ አሕሥሞ ፡ እስመ ፡ ልማዶሙ ፡ ወፍጥረቶሙ ፡ ፍሉጥ ፡ በአዝማናቲሆሙ ፡ ወናሁ ፡ ቦአ ፡ ተሚሚጸ፡ እምነ ፡ ዝንቱ ፡ ዘይነግር ፡ ከሊአ ፡ ተሠርግዎ ፡ ሥጋዊ ።

፩ሺ፯፻፺፪ በዚህም ፡ ወንዶችን ፡ ከሴቶች ፡ ጋራ ፡ መጥቀስን ፡ አልተውንም ። ስለ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ልማዳቸው ። በዘመናቸው ፡ ልማዳቸውና ፡ ተፈጥሮዋቸው ፡ ልዩ ፡ ነበረና ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ሥጋዊ ፡ ጌጥን ፡ መከልከልን ፡ የሚናገር ፡ ምክር ፡ እነሆ ፡ ተሠራ ።

፩ሺ፯፻፺፫ ወናሁ ፡ ስምዑ ፡ ኮነ ፡ ባስልዮስ ፡ ከመ ፡ ቃለ ፡ ሐዋርያ ፡ ውስተ ፡ ተናገረ ፡ ዘጽሑፈ ፡ "ወይቤ ፡

፩ሺ፯፻፺፫ እንደ ፡ ሐዋርያ ፡ ቃል ፡ በጻፈው ፡ ትእዛዝ፡ ባስልዮስ ፡ እነሆ ፡ ምስክር ፡ ሆነ ፡ ሐዋርያ ፡

ኢይኅድግ ፡ ብእሲ ፡ ሥዕርቶ ፡ ከመ ፡ ይኑኅ ፡ ለግሙራ ፡ ከመ ፡ ቃለ ፡ ሐዋርያ ፡ ወይደሉ ፡ ሳጽ ዮቱ” ። ወከመ ፡ ቃለ ፡ ሐዋርያት ፡ በዮንተ ፡ ዲድስቅልያ ፡ ዘይቤሉ ፡ ኢታንኅ ፡ ሥዕርተ ፡ ርእስከ ፡ ወኢትሕፅዋ ፡ ወኢትቅብእ ፡ ዕፍረተ ፡ ወኢትኅድጎ ፡ ስፉሐ ፡ ኢፍቱለ ፡ ወኢዕፉረ ፡ ወኢትረሲ ፡ ለከ ፡ ድንጉዛተ ፡ ወነኮላለ ፡ አላ ፡ ላጽዮ ፡ ወእጽሪ ፡ ርእስከ ። ወኢትሠርገው ፡ በሠርጕ ፡ ዘትፈትወከ ፡ ባቲ ፡ ብእሲት ፡ ወትከውን ፡ ኃጥእ ፡ በኃጢእታ ።

እንደተናገረው ፡ ወንድ ፡ ከቶ ፡ ጠጉሩን ፡ ያድግ፡ ዘንድ ፡ አይተወው ። ሲላጨትም ፡ ይገባል ፡ አለ ። በዲድስቅልያ ፡ መጀመሪያ ፡ እንደተነገ ረው ፡ እንደ ፡ ሐዋርያት ፡ ቃልም ፡ የራስህን ፡ ጠጉር ፡ አታሳድግ ። አትከባክበው ፡ ሽቱም ፡ አትቀባው ። ግልስልስ ፡ አታድርገው ፡ ወይም ፡ የተፈተለ ፡ ወይም ፡ የተጐነጐነ ፡ አድርገህ ፡ አት ተወው ። ሽርቤ ፡ ስርሜዶ ፡ አታድርግ ። ላጨው እንጂ ፡ ራስህንም ፡ አጥራ ። ሴት ፡ አንተን ፡ በም ትወድበት ፡ ጌጥ ፡ አታጊጥ ። በእርሱዋም ፡ ኃጢ አት ፡ አንተ ፡ ኃጢአተኛ ፡ ትሆናለህ ።

፩ሺ.፪፻፺፱ ወጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ናሁ ፡ ገብረ ፡ ዘንተ ፡ በርእሱ ፡ ፪ተ ፡ ጊዜያተ ፡ በከመ ፡ ስምዐ ፡ ኮነ ፡ መጽሐፈ ፡ አብረክሲስ ፡ ወ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ብፅዓት ፡ ኮነ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወብፅዐትሰ ፡ ዘእግዚ አብሔር ፡ ኢይከውን ፡ ዘእንበለ ፡ በገቢረ ፡ ትሩ ፋት ፡ ወፈድፋደሰ ፡ መኑ ፡ ከመ ፡ ገብረ ፡ ሐዋ ርያ ፡ ዘጽኑዕ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወበጽድቅ ። ወአልቦ ፡ ኑፋቄ ፡ ወካሕድ ፡ ከመ ፡ ገቢረ ፡ ብፅ ዐቲ ፡ ለሐዋርያ ፡ ትሩፍ ፡ ሕግ ፡ ኮነ ፡ ለዘሉፉ ፡ ለሰብእ ፡ ጽዋዔሁ ፡ ዘናሁ ፡ ገብረ ፡ ትሩፋተ ።

፩ሺ.፪፻፺፱ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስም ፡ እነሆ፥ ይህን ፡ በራሱ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ አደረገ ፡ የሐዋርያት ፡ መጽሐፍ ፡ (ሥራ) ፡ እንደመሰከረ ፡ (የሐዋ ፡ ፲፰ ፡ ፲፰ ። ፳፩ ፡ ፳፬ ።) ከእነርሱም ፡ አንዱ ፡ ብፅዓት ፡ ነበ ረበትና ፡ ነው ። ለእግዚአብሔርም ፡ የሚሆን ፡ ብፅዓት ፡ ትሩፋት ፡ በመሥራት ፡ ካልሆነ ፡ በቀ ር ፡ አይሆንም ፡ ይልቁንም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስና፡ በእውነት ፡ እንደዚህ ፡ ሐዋርያ ፡ ያለ ፡ ማነው ? ፍጹም ፡ ሐዋርያ ፡ እሁን ፡ ትሩፋት ፡ አደርጎ ፡ የሠራው ፡ ብፅዓቱን ፡ መፈጸሙ ፡ ለጠራቸው ፡ ሰዎች ፡ ለዘለዓለሙ ፡ ሕግ ፡ እንደሆነ ፡ ጥርጥ ርና ፡ ክህደት ፡ የለበትም ።

፩ሺ.፫፻ ወቃልኒ ፡ ዘተነግረ ፡ ውስተ ፡ ቀኖናቲሆሙ ፡ ለጉባኤ ፡ ኒቅያ ፡ ዘጕላቂሆሙ ፡ ፫ ፡ እምድኅረ ፡ ፫ ፡ ዘይብል ፡ ኢያስተርኢ ፡ ሥዕርትከ ፡ በአ ፍአ ፡ እስመ ፡ ናሁ ፡ ሐዋርያ ፡ ከልአ ፡ ዘንተ ፡ አምሳለ ። ወኢትንሣእ ፡ እምጸጕረ ፡ ጽሕምከ ፡ ጊዜ ፡ ትላጺ ፡ ሥዕርተ ፡ ርእስከ ፡ ወኢትኅድግ ፡ ላዕሌከ ፡ ሥርጋዌ ፡ እምጸጕረ ፡ ርእስከ ።

፩ሺ.፫፻ ከኻያ ፡ በኋላ ፡ ቍጥራቸው ፡ ኻያ ፡ በሚሆን ፡ በኒቅያ ፡ ጉባኤ ፡ መጻሕፍት ፡ የተነገረው ፡ ቃልም ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ነው ። ጠጉርህ ፡ በአፍአ ፡ (በውጭ) ፡ አይታይ ። ሐዋርያ ፡ ይህን፡ አርአያ ፡ ከልክሎአልና ። ራስህን ፡ በምትላጭበ ትም ፡ ጊዜ ፡ ከጽሕምህ ፡ ፀጉር ፡ አትንሣለት ። ከራስህ ፡ ፀጉርም ፡ ለጌጥ ፡ አትተውለት ።

፩ሺ.፫፻፩ ወጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ወጉባኤ ፡ ዘማንግራ ፡ ሶበ ፡ ከልእዎን ፡ ለአንስት ፡ እምላጸዮ ፡ ጸጕ ሮን ፡ አዘዝዎን ፡ ለባሕቲቶን ፡ ዘእንበለ ፡ እደው ።

፩ሺ.፫፻፩ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስና ፡ የግንግራ ፡ ጉባኤ ፡ ሴቶ ችን ፡ ጠጉራቸውን ፡ ከመላጨት ፡ በከለከሏ ቸው ፡ ጊዜ ፡ ከወንዶች ፡ ለይተው ፡ ብቻቸውን ፡ አዘዟቸው ።

፩ሺ.፫፻፪ ወበእንተ ፡ ግዝረትሰ ፡ እምትእዛዝ ፡ ብሉይ ፡ ውእቱ ፡ ተሠርዐ ፡ ከመ ፡ ይትፈለጡ ፡ ሕዝበ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምኵሉ ፡ አሕዛብ ፡ በከመ ፡ ይትኀተሙ ፡ እግብርት ፡ ለመላኪሆሙ ። ወበ እንተዝ ፡ ኢይደሉ ፡ ተሰምዮ ፡ ዘእንበለ ፡ እም ድኅረ ፡ ግዝረት ። ወይመርሕ ፡ ላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ ቃለ ፡ ሉቃስ ፡ በውስተ ፡ ወንጌል ፡ በእንተ ፡ ዮሐንስ ፡ ወእግዚእነ ፡ ዘይቤ ፡ መጽኡ ፡ ኀበ ፡ ሕፃን ፡ ከመ ፡ ይግዝርዎ ፡ ወሰመይዎ ፡ ስሞ ።

፩ሺ.፫፻፪ ስለ ፡ ግዝረትም ፡ ከብሉይ ፡ ትእዛዝ ፡ ወገን ፡ ነው ። ባሮች ፡ ለጌቶቻቸው ፡ እንደሚከተቡ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወገኖች ፡ ከአሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ይለዩ ፡ ዘንድ ፡ ታዘዘ ። ስለዚህ ፡ ከግዝረት ፡ በኋላ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ስም ፡ ማውጣት ፡ አይገ ባም ። በዚህም ፡ ላይ ፡ ሉቃስ ፡ በወንጌል ፡ ስለዮ ሐንስና ፡ ስለጌታችን ፡ ይገዝሩት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ሕፃኑ ፡ መጡ ፡ ስሙንም ፡ አወጡለት ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ያስረዳል ። (ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፶፱ ። ፪ ፡ ፳፩) ።

አንቀጽ ፡ ፶፩ ።

፩ሺ፫፻፫ ወሶበ ፡ አስተጋብአት ፡ ሕግ ፡ መሢሓዊት ፡ ኵሎ ፡ አሕዛበ ፡ ተጋብረት ፡ ለብእሲ ፡ ዘተፈጥረ ፡ በነፍስ ፡ ወሥጋ ፡ ተሰምዮ ፡ መንፈሳዊት ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ጥምቀት ፡ በዘባቲ ፡ ይትፈለጡ ፡ መሢሓውያን ፡ እምካልአሙ ፡ ወረሰዩ ፡ ሎቱ ፡ ተሰምዮተ ፡ ስሙ ፡ በጊዜ ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ በከመ ፡ ያወፅኡ ፡ ወያነብሩ ፡ አጋእዝት ፡ ስመ ፡ ለአግብርቲሆሙ ።

፩ሺ፫፻፬ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ግብር ፡ በአሐቲ ፡ ምክንያት ፡ ኀበ ፡ አዳም ፡ ብእሲት ፡ ቀዳማዊት ፡ ከመ ፡ ይሰምያ ፡ በእንተ ፡ ኰንኖቱ ፡ ኪያሃ ፡ ወእማዚእናሁ ፡ ላዕሌሃ ። ወበዝቱ ፡ ፋና ፡ በአሐቱ ፡ ፍጥረተ ፡ እንስሳ ፡ ኀበ ፡ አዳም ፡ ከመ ፡ ይሰምዮሙ ፡ ትእምርተ ፡ በእንተ ፡ ኰንኖቱ ፡ ኪያሆሙ ፡ ወእማዚእናሁ ፡ በላዕሌሆሙ ።

፩ሺ፫፻፭ ወበሕግስ ፡ ሐዲስ ፡ እስመ ፡ ግዝረት ፡ ኀበ ፡ ዘይትገበር ፡ እምበዓለ ፡ ግዝረት ፡ በከመ ፡ ፋና ፡ ልማድ ፡ አኮ ፡ እምፍና ፡ ቀኖና ፡ ሕጋዊ ። ወከመዝ ፡ ውእቱ ፡ ተነግረ ፡ ግብሩ ፡ ውስተ ፡ አሪት ፡ በሳምን ፡ ዕለት ፡ እምዕለተ ፡ ልደቱ ፡ ለዘይትገዝር ፡ ወይእቲ ፡ እመ ፡ ካልእ ፡ አምሳምንት ፡ ኢትትኀለቍ ፡ እምግዝረቱ ፡ ሕጋዊት ። ወእለ ፡ ይገብርዋ ፡ እምሰብአ ፡ ሐዲስ ፡ ሕግ ፡ ኢይገብርዋ ፡ በሳምን ፡ ዕለት ፡ ወኢየኀርዩ ፡ ዘንተ ።

፩ሺ፫፻፮ ወግዝረትሰ ፡ ዘነበኒ ፡ ይደሉ ፡ ኀዲጎታ ፡ ወይደሉ ፡ ገቢሮታ ፡ ዘእንበለ ፡ ውሳኔ ፡ ዘሕግ ። ወትምእርተ ፡ ዝንቱ ፡ ቃለ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ በውስተ ፡ ምዕራፍ ፡ ሳብዕ ፡ እምን ፡ መልእክቱ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀበ ፡ ሰብአ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ወይቤ ፡ "ኢኮነ ፡ ግዝረት ፡ ምንተኒ ፡ ወቍልፈትኒ ፡ ዳእሙ ፡ ኵይድቅስ ፡ ዐቂበ ፡ ትእዛዘ ፡ እግዚአብሔር ። ወብዝኀሎቱ ፡ ካዕበ ፡ ለሰብአ ፡ ገላትያ ፡ ዘኃምስ ፡ እምኔሃ ፡ "ተገዝሮኒ ፡ ኢይበቍዕ ፡ ወኢተገዝሮኒ ፡ አላ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘይትፌጸም ፡ በፍቅር ። ወይቤ ፡ ዘንተ ፡ ቃለ ፡ በክፍል ፡ ሳድስ ፡ እምኔሃ ፡ ወይቤ ፡ ኢኮነ ፡ ግዝረት ፡ ምንተኒ ፡ ወኢቍልፈት ፡ አላ ፡ በቀዲሙ ፡ ግብርሰ ፡ ፍጥረት ፡ ሐዲስ ፡ ዘውእቱ ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትና ።

ስለ ፡ ጠንርና ፡ ስለ ፡ ግዝረት ።

፩ሺ፫፻፫ የክርስቶስ ፡ ሕግ ፡ አሕዛብን ፡ ሁሉ ፡ በሰበሰበች ፡ ጊዜ ፡ በነፍስና ፡ በሥጋ ፡ ለተፈጠረ ፡ ሰው ፡ መንፈሳዊት ፡ ስም ፡ ተደረገች ። ይህችውም ፡ ክርስቲያኖች ፡ ከሌሎቻቸው ፡ የሚለዩባት ፡ ጥምቀት ፡ ናት ። የስሙ ፡ አወጣጥ ፡ በጥምቀት ፡ ክርስትና ፡ ጊዜ ፡ እንዲሆን ፡ አደረጉ ። ጌቶች ፡ ለባሮቻቸው ፡ ስም ፡ አውጥተው ፡ እንዲያኖሩ ።

፩ሺ፫፻፬ ስለዚህም ፡ ሥራ ፡ ምክንያት ፡ እርሱ ፡ እርሱዋን ፡ ስለሚገዛት ፡ ጌትነቱም ፡ በእርስዋ ፡ ላይ ፡ ስለሆነ ፡ ስም ፡ ያወጣላት ፡ ዘንድ ፡ የቀደመችው ፡ ሴት ፡ ወደአዳም ፡ ሄደች ። በዚችም ፡ መንገድ ፡ ፍጥረተ ፡ እንስሳ ፡ እነርሱን ፡ ስለሚገዛቸው ፡ ጌትነቱም ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ስለሆነ ፡ በምልክታቸው ፡ ስም ፡ ያወጣላቸው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ አዳም ፡ መጡ ። (ዘፍ ፡ ፪ ፡ ፲፱ - ፳ ። ፫ ፡ ፳ ።)

፩ሺ፫፻፭ በሐዲስ ፡ ሕግ ፡ ግን ፡ ከገዛሪ ፡ የሚደረግ ፡ ግዝረት ፡ በልማድ ፡ ጎዳና ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሕጋዊ ፡ ከሆነ ፡ ከትእዛዝ ፡ ወገን ፡ አይደለም ። ሥርዓቷ ፡ የሚገዘረው ፡ ሰው ፡ ከተወለደበት ፡ ቀን ፡ ጀምሮ በስምንተኛው ፡ ቀን ፡ እንዲሆን ፡ በኦሪት ፡ እንደዚህ ፡ ተነገረ ። ከስምንት ፡ ቀን ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ የሆነች ፡ ግዝረት ፡ ከግዝረት ፡ ወገን ፡ ሕጋዊት፡ ሁና ፡ አትቆጠርም ። ከሐዲሱ ፡ ሕግ ፡ ሰዎች ፡ ወገን ፡ የሚሠሩዋትም ፡ በስምንት ፡ ቀን ፡ አያደርጓትም ። ይህንም ፡ ዕለት ፡ አይመርጡም ።

፩ሺ፫፻፮ ግዝረት ፡ ግን ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ ሊተዋት ፡ ይገባል ። ያለ ፡ ሕግ ፡ ውሳኔም ፡ ሊሠሯት ፡ ይገባል ። የዚህም ፡ ምልክቱ ፡ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ ለቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ በጻፈው ፡ በመጀመሪያ ፡ መልእክቱ ፡ በ፯ኛው ፡ ምዕራፍ ፡ መገዘር ፡ ወይም ፡ አለመገዘር ፡ ምንም ፡ አይደለም ። ጽድቅስ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ መጠበቅ ፡ ነው ፡ አለ ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፲፰ - ፳) ። ዳግመኛም ፡ ለገላትያ ፡ ሰዎች ፡ በጻፈው ፡ በ፭ኛው ፡ ምዕራፍ ፡ የሚጠቅም ፡ በፍቅር ፡ የተፈጸመ ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መገዘርም ፡ አለመገዘርም ፡ አይጠቅምም ፡ ያለው ፡ ነው ። ይህንም ፡ ቃል ፡ ከእርስዋ ፡ በ፮ኛው ፡ ክፍል ፡ መገዘር ፡ ወይም ፡ አለመገዘር ፡ ምንም ፡ አይደለም ። የሚጠቅም ፡ ሥራ ፡ ሐዲስ ፡ ፍጥረት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ደገመው ። ይኸውም ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡

፩ሺ፰፻፺፯ ወቃላቲሁሰ ፡ እንተ ፡ ትትከሠት ፡ እምእፉአ ፡ ትንግር ፡ ከሢአ ፡ ግዘረት ፡ እስመ ፡ ኮነ ፡ መፍቅዱ ፡ ባቲ ፡ ከሢአ ፡ እምተአኅዞ ፡ በሕገ ፡ ኦሪት፡ ዘጥንተ ፡ ዚአሃ ፡ ትእዛዘ ፡ ግዝረት ። ወስመየ ፡ ስሕግ ፡ በጥንተ ፡ ዚአሃ ፡ በከመ ፡ ተሰምየ ፡ መጻሕፍት ፡ በጥንቶሙ ፡ ዘውእቶሙ ፡ መጽሐፈ ፡ ፍጥረት ፡ ወመጽሐፈ ፡ ኍልቈ ። ወበከመ ፡ ዝንቱ ፡ ፍኖት ፡ ተሰምየት ፡ ሕገ ፡ ኦሪት ፡ በስመ ፡ ግዘረት ፡ ውስተ ፡ መካን ፡ ዘዘከር ፡ ወተሰምየት ፡ ካልእታ ፡ በቍልፈት ። ወዘይመርሕ ፡ ላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ ቃሉ ፡ ዘውስተ ፡ ምስራፍ፡ ሳብዕ ፡ ለስብአ ፡ ቆሮንቶስ ፡ "ለእመ ፡ ተጸውዐ፡ ብእሲ ፡ ኀበ ፡ ሃይማኖት ፡ እንዘ ፡ ግዙር ፡ ውእቱ፡ ኢይግባእ ፡ ኀበ ፡ ቍልፈት" ።

፩ሺ፰፻፺፰ ወአፍአሁ ፡ ለዝንቱ ፡ ቃል ፡ እመስ ፡ ውእቱ ፡ አመረ ፡ ኀበ ፡ ተገዝሮ ፡ በዝከር ፡ በሕገ ፡ ግዝረት ፡ ዘውእቱ ፡ መተረ ፡ ሥጋ ፡ ስምንትኑ ፡ ይብ ፡ ኢይግባእ ፡ ኀበ ፡ ቍልፈት ፡ እስመ ፡ ኢይትከሀሎ ፡ ለግዙር ፡ ከመ ፡ ይትመየጥ ፡ ኀበ ፡ ከዊነ ፡ ኢግዙር ፡ ወያጸንዕ ፡ ዘንተ ፡ ቃለ ፡ በመልእክቱ ፡ ኀበ ፡ ሰብአ ፡ ሮሜ ፡ በብሂሉቱ ፡ ለእመ ፡ እመንከ ፡ አ ፡ ብእሲ ፡ ወተዓቀብከ ፡ ሕገ ፡ ኦሪት ፡ ይከውን ፡ ግዘረትከ ፡ ቍልፈተ ፡ ወእመሰ እንዘ ፡ ቈላፍ ፡ አንተ ፡ ወዐቀብከ ፡ ሕገገ ፡ ኦሪት፡ ቍልፈትከ ፡ ግዝረተ ፡ ትከውነከ ፡ ወትትፌጸም ፡ ላዕሌከ ፡ ቍልፈት ፡ ዘይፈጽማ ፡ በኀበ ፡ ሕግ ፡ እምጠባይዒሁ ።

፩ሺ፰፻፺፱ ወበእማን ፡ ኢይደሉ ፡ ተገዝሮ ፡ እምድኅረ ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትና ። ወዘይመርሕስ ፡ ላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ ፍጻሜ ፡ ቃሉ ፡ በእንተ ፡ ግዝረት ፡ ዘተናገረ ፡ ለስብአ ፡ ቆሮንቶስ ፡ "ወይብል ፡ የሀሉ ፡ ኵሉ ፡ ብእሲ ፡ እምኔክሙ ፡ በግብር ፡ ዘተጸውዐ ፡ ባቲ ፡ ኀበ ፡ ሃይማኖት" ። ወካዕበ ፡ እመስ ፡ ኮነ ፡ ተገዝሮ ፡ ዘኢይደሉ ፡ ግሙራ ፡ እምኢያብሖ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ለጢሞቴዎስ ፡ ኤጺስቆጳስ ፡ ረድኡ ፡ በከመ ፡ ስምዐ ፡ ኮነ መጽሐፈ ፡ እብረክሲስ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ገዘሮ ።



ነው ። (ገላ ፡ ፫ ፡ ፯ ። ፲፫ - ፲፯) ።

፩ሺ፰፻፺፯ በአፍአ ፡ የምትገለጽ ፡ ትምህርቱ ፡ ግን ፡ ከግዝረት ፡ መከልከልን ፡ ትናገራለች ። ፈቃዱ ፡ መሠረቱ ፡ የግዝረት ፡ ትእዛዝ ፡ በሆነ ፡ በኦሪት ፡ ትእዛዝ ፡ ከመያዝ ፡ መከልከል ፡ ነበረና ። ኦሪትንም ፡ በጥንተ ፡ ስሟ ፡ ጠራት ። መጻሕፍት ፡ በጥንተ ፡ ስማቸው ፡ እንደተጠሩ ። እነርሱም ፡ ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ ኦሪት ፡ ዘኍልቈ ፡ ናቸው ። በእንደዚህም ፡ ያለ ፡ መንገድ ፡ በተነገረው ፡ አንቀጽ ፡ የኦሪት ፡ ሕግ ፡ በግዝረት ፡ ስም ፡ ተጠራች ። ሁለተኛዋም ፡ ቍልፈት ፡ ተብላ ፡ ተጠራች ። በዚህም ፡ ላይ ፡ የሚያስረዳ ፡ ለቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ በጻፈው ፡ በ፯ኛው ፡ ምስራፍ ፡ ሰው ፡ የተገዘረ ፡ ሆኖ ፡ ወደ ፡ ሃይማኖት ፡ ቢጠራ ፡ ወደ ፡ ቍላፍነት ፡ አይመለስ ። ያለው ፡ ቃል ነው ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፲፰)።

፩ሺ፰፻፺፰ የዚህ ፡ ቃል ፡ አፍአዊ ፡ ንባቡ ፡ በግዝረት ፡ ሕግ ፡ ወደ ፡ ተነገረ ፡ መገዘር ፡ የሚያመለክት ፡ ከሆነ ፡ ይኸውም ፡ ሥጋን ፡ መቍረጥ ፡ ነው ። የተገዘረ ፡ ሰው ፡ ያልተገዘረ ፡ ወደመሆን ፡ ይመለስ ፡ ዘንድ ፡ አይቻለውምና ፡ ወደ ፡ አለመገዘር፡ አይመለስ ፡ ለምን ፡ አለ ? ይህንም ፡ ቃል ፡ ሰው፡ ሆይ ፡ ብታምን ፡ ሕገ ፡ ኦሪትንም ፡ ካፈረስከ ፡ ግዝረትህ ፡ ቍልፈት ፡ (አለመገዘር) ፡ ይሆንብሃል ፡ ብሎ ፡ ለሮም ፡ ሰዎች ፡ በጻፈው ፡ መልእክቱ ፡ ያስረዳል ። በቈላፍነት ፡ ሳለህ ፡ ሕገ ፡ ኦሪትን ፡ ብትጠብቅ ፡ ግን ፡ ቍልፈትህ ፡ (አለመገዘርህ) ፡ ግዝረትን ፡ ትሆንልሃለች ። በዓለ ፡ ሕግ ፡ ሰው ፡ ከባሕርዩ ፡ የሚፈጽማት ፡ ቍልፈትም ፡ ትፈጸምልሀለች ። (ሮሜ ፡ ፪ ፡ ፳፭ - ፳፱) ።

፩ሺ፰፻፺፱ ከክርስትና ፡ ጥምቀት ፡ በኋላ ፡ መገዘር ፡ በእውነቱ ፡ አይገባም ። በዚህም ፡ ላይ ፡ የሚያስረዳ ፡ ለቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ግዝረት ፡ የተናገረው የመጨረሻ ፡ ቃሉ ፡ ነው ። ከእናንተ ፡ ሰዉ ፡ ሁሉ ፡ ወደሃይማኖት ፡ በተጠራበት ፡ ግብር ፡ ጸንቶ ፡ ይኑር ፡ አለ ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፳) ። ዳግመኛም ፡ መገዘር ፡ ፈጽሞ ፡ የማይገባ ፡ ቢሆንስ ፡ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ ለደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ባልፈቀደለትም ፡ ነበር ። (ባልገዘረውም ፡ ነበረ) ፡ የሐዋርያት ፡ ሥራ ፡ እርሱ ፡ እንደገዘረው ፡ ምስክር ፡ እንደ ሆነ ። (የሐዋ ፡ ፲፮ ፡ ፫ ።)

## አንቀጽ ፡ ፶፩ ።

፩ሺ፰፻፲ ወለእመ ፡ ተብህለ ፡ እስመ ፡ ዕጹብ ፡ አገበሮ ፡ በእንተ ፡ ግዝረት ፡ ይከውን ፡ እውሥአትነ ፡ ከመ ፡ ግብር ፡ ሕጋዊት ፡ ትትከፈል ፡ ኀበ ፡ ፪ኤ ፡ ክፍል ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ፍትሕ ፡ ዘይደሉ ፡ ገቢሮቱ ፡ ወኢይደሉ ፡ ኀዲጎቱ ፡ በኵሉ ፡ ግብር ፡ ወበኵሉ ፡ ዘመን ፡ በእንተ ፡ ዘአዘዘ ፡ ቦቱ ፡ ወኢ ከልአ ፡ እምኔሁ ። ወቦ ፡ ትእዛዝ ፡ ዘከመ ፡ ጥምቀት ፡ ክርስትና ፡ እንተ ፡ ዘእንበሌሁ ፡ ኢይትረከብ ፡ መንግሥተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዘከመ ፡ ተዋሕዶት ፡ እምላካዊት ፡ ወትሥልስተ ፡ አካላቲሁ ። በከመ ፡ ይቤ ፡ ጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ "መልአክ ፡ እምሰማይ ፡ አው ፡ ካልእ ፡ እመ ፡ መሀረክሙ ፡ ካልአ ፡ እምዘመሀርናክሙ ፡ ንሕነ ፡ ውጉዘ ፡ ለይኩን" ። ወተግሣጽሰ ፡ በእንተ ፡ ቀቲል ፡ ወዝሙት ፡ ይቤ ፡ ከመ ፡ እለ ፡ ይገብሩ ፡ እሎንተ ፡ ሀቢያተ ፡ ኢይወርስዋ ፡ ለመንግሥተ ፡ እግዚአብሔር ።

፩ሺ፰፻፲፩ ወዳግምኒ ፡ ዘይደሉ ፡ ገቢሮቱ ፡ ወኀዲጎቱ ፡ ዘከመ ፡ ጸሎት ፡ ወጾም ፡ ዘወትር ፡ ወተገዝሮ ፡ ዘስምዐ ፡ ኮነ ፡ ከመ ፡ ድልው ፡ ውእቱ ፡ በ፪ኤ ፡ ፍና ፡ በከመ ፡ አቅደምነ ፡ ዘክሮ ፡ ወዘይመስሎ ፡ ኪያሁ ፡ እምግብረት ፡ ዘልማድ ። ወለኵሎሙ ፡ አሕዛብ ፡ ሀለዎሙ ፡ ምግባራት ፡ ዘልማድ ፡ ዘትግሕ ፡ በኀቤሆሙ ። ወቦ ፡ ዘትከውን ፡ ኅሣረ ፡ በኀበ ፡ ካልአኒሃ ፡ ከመ ፡ ቀሪጸ ፡ ገጽ ፡ በኀበ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወሮባ ፡ ወከመ ፡ ተላጽዮ ፡ ጽሕም ፡ በኀበ ፡ አፍርንጅ ፡ ወከመ ፡ ካህናተ ፡ ሮም ፡ እለ ፡ ይላጸዩ ፡ ማእከለ ፡ አርእስቲሆሙ ። ወእሙኒ ፡ ይቤሉ ፡ እሉ ፡ ፪ቱ ፡ መዓርጋት ፡ ከመ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳቲሆሙ ፡ እዘዝዎሙ ፡ በዝንቱ ፡ ንብሎሙ ፡ ወከማሁ ፡ ቅብጣውያንሂ ፡ እለ ፡ ይትገዘሩ ፡ እብሕዎሙ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳቲሆሙ ፡ ከመ ፡ ይትገዘሩ ።

፩ሺ፰፻፲፪ ወቦ ፡ ዘይቤ ፡ ዘከመ ፡ ገብረ ፡ ሐዋርያ ፡ ግዝረተ ፡ በእንተ ፡ መፍቅድ ፡ ወበቍዔት ፡ ከማሁ ፡ ገብሩ ፡ ቅብጣውያን ፡ በእንተ ፡ መፍቅድ ፡ ወበቍዔት ። ወመፍቅድሰ ፡ በእንተ ፡ ዘኮኑ ፡ ኀዱራነ ፡ ማእከለ ፡ ግዙራን ፡ ወናሁ ፡ ጸኑ ፡ ወረሰዩቶሙ ፡ ኀበ ፡ ምግባራት ፡ እኩያት ፡ እስከ ፡ ይትገዘሩ ፡ እምድኅረ ፡ ነሢአ ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ ወእምነ ፡ ዝንቱ ፡ ይትዐቀቡ ። ወካል

## ስለ ፡ ጠጉርና ፡ ስለ ፡ ግዝረት ።

፩ሺ፰፻፲ ጭንቅ ፡ ነገር ፡ አስገድዶት ፡ ነው ፡ እኮ ፡ ቢባልም ፡ መልሳችን ፡ በሕግ ፡ የምትሠራ ፡ ሥራ ፡ ከሁለት ፡ እንደምትከፈል ፡ ይሆናል ። ከእነርሱም ፡ አንዱ ፡ ሊያደርጉት ፡ የሚገባ ፡ በሥራውም ሁሉ ፡ በዘመኑም ፡ ሁሉ ፡ ሊተውት ፡ የማይገባ ፡ ፍርድ ፡ ነው ። እርሱን ፡ ስለአዘዘ ፡ ከእርሱም ፡ ስለ ፡ እልከለከለ ፡ ሌላ ፡ ትእዛዝም ፡ አለ ። ይኸውም ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ያለ ፡ እርሱ ፡ የማይገኝ ፡ እንደ ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትና ፡ እንደ ፡ እምላካዊት ፡ ተዋሕዶ ፡ እንደ ፡ እካላትም ፡ ሦስትነት ፡ ያለ ፡ ነው ። ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ መልአክ ፡ ከሰማይ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ እኛ ፡ ካስተማርናችሁ ፡ ሌላ ፡ ያስተማራችሁ ፡ ቢኖር፡ የተለየ ፡ ይሁን ፡ እንዳለ ። (ገላ ፡ ፩ ፡ ፰) ። ስለ መግደልና ፡ ስለ ፡ ዝሙት ፡ ቀጣት ፡ ግን ፡ እሊህን ፡ ታላላቅ ፡ ኃጣውእ ፡ የሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ አይወርሱዋትም ፡ አለ ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፱ - ፲፩) ።

፩ሺ፰፻፲፩ ሁለተኛውም ፡ ሊሠሩትና ፡ ሊተዉት ፡ የሚገባ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ እንደ ፡ ዘወትር ፡ ጸሎትና ፡ ጾም ፡ ያለ ፡ ነው ። አስቀድመን ፡ እንደተናገርን ፡ በሁለት ፡ ወገን ፡ የመሰከሩለት ፡ ግዝረትና ፡ ከልማድ ፡ ሥራዎች ፡ ወገን ፡ እርሱንም ፡ የሚመስለው ፡ ነው ። ለአሕዛብም ፡ ሁሉ ፡ በእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ የምትሻ ፡ የልማድ ፡ ሥራዎች ፡ አሏቸው ። በሌሎች ፡ ዘንድ ፡ ተዋርዶ ፡ የምትሆን ፡ ሥራም ፡ አለች ። በኢትዮጵያና ፡ በሮባ ፡ ዘንድ ፡ ፊትን ፡ እንደመተፋተፍ ፡ በአፍርንጅም ዘንድ ፡ ጽሕምን ፡ እንደመላጨት ፡ እንደ ፡ ሮም ካህናትም ፡ መሃል ፡ ራሳቸውን ፡ እንደሚላጩት ፡ ያለ ፡ ነው ። እሊህ ፡ ሁለቱ ፡ መዓርጋትስ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳቶቻቸው ፡ ይህን ፡ አዝዘዋቸው ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ የሚገዘሩ ፡ ግብጾችም ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳቶቻቸው ፡ እንዲገዘሩ ፡ አዝዘዋቸው ፡ ነው ፡ እንላቸዋለን ።

፩ሺ፰፻፲፪ ሐዋርያ ፡ ግዝረትን ፡ ስለፈቃድና ፡ ስለጥቅም ፡ እንደ ፡ አደረገው ፡ ግብጻውያንም ፡ ስለ ፡ ፈቃድና ፡ ስለጥቅም ፡ አደረጉት ፡ የሚል ፡ አለ ። መፍቅድስ ፡ በግዙራን ፡ መካከል ፡ የሚኖሩ ፡ ስለሆኑና ፡ ጎልማሶቻቸውም ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትናን ፡ ከመቀበል ፡ በኋላ ፡ እስኪገዘሩ ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ እነሆ ፡ ስለአዘነበሉ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ ግን ፡ ይጠበቁ ። እነሆ ፡

አት ፡ መፍቅዳት ፡ ዘናሁ ፡ ዘከርምን ፡ በካልእ ፡ እምዝንቱ ፡ መጽሐፍ ።

፩ሺ፰፻፲፫ ወበእንተ ፡ በቍዔትስ ፡ ናሁ ፡ ዘከረ ፡ ፩ዱ ፡ ጠቢብ ፡ እምፈላስፋ ፡ እለ ፡ የአምሩ ፡ ጥበበ ፡ ዘበበገጹ ፡ ወይቤ ፡ እስመ ፡ በተገዝሮ ፡ ይደክም ፡ ንዋየ ፡ ፍትወት ፡ ወየሐጽጽ ። ወዝንቱሂ ፡ በተሰናዕዎ ፡ ድልው ፡ ውእቱ ፡ በዛቲ ፡ ሥርዓት ፡ ቅድስት ።

፩ሺ፰፻፲፬ ወተአምኖ ፡ ኃጢውእስ ፡ ፈውስ ፡ መንፈሳዊ ፡ ውእቱ ፡ ወተሰምዮቱሂ ፡ በመንፈስ ፡ ዘያስተዛምድ ፡ ምስለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በከመ ፡ ተዘምዶ ፡ ሥጋዊ ፡ ያስተሳትፍ ፡ ምስለ ፡ ሥጋ ። ወበከመ ፡ ፈውስ ፡ ሥጋዊ ፡ ኢይትፌጸም ፡ ዘእንበለ ፡ በእደ ፡ ዐቃቤ ፡ ሥራይ ፡ ጠቢብ ፡ ወኄር ፡ ወእመ ፡ እኩስ ፡ ኅዲግ ፡ ተፈውሶ ፡ ይኄይስ ፡ እምተፈውሶ ፡ በእደ ፡ ዐብድ ፡ ወእኩይ ። ወዓዲ ፡ በተወክፎተ ፡ ድውይ ፡ ዘይገብሩ ፡ ሎቱ ፡ ዘይፈውሶ ፡ እምዘይቤልዎ ። ወካዕበ ፡ በዘይትከሀሎ ፡ ፈውሶት ፡ በከዊነ ፡ ዘመን ፡ ወመካን ፡ ወክሂል ፡ ወእመ ፡ አኮሰ ፡ አልቦቱ ፡ በቍዔት ፡ ወከማሁ ፡ መንፈሳዊኒ ።

፩ሺ፰፻፲፭ ወእምከመ ፡ ኢተረክበ ፡ ማእምረ ፡ ፈውስ ፡ ኢትመጽእ ፡ ሠናይት ፡ ወከማሁ ፡ በዜቱ ፡ ክፍል ፡ ኮነ ፡ ተአምኖ ፡ ኃጢውእ ፡ ዘይትፈቀድ ፡ ኢይትረከብ ፡ ውስተ ፡ ገጽ ፡ ዘእንበለ ፡ በንስቲት ። ወቦ ፡ እምሊቃን ፡ ጳጳሳቲሆሙ ፡ እለ ፡ ከልኡ ፡ ኪያሁ ፡ በዓለም ፡ በእንተ ፡ ተኃጥአተ ፡ አኀብሮቶሙ ፡ ለዚቱ ፡ ውሳኔያት ፡ ዘኢይትፌጸም ፡ በሠናይ ፡ ዘእንበለ ፡ ባቲ ። ወበከመ ፡ ኢኮኑ ፡ ኵሎሙ ፡ ሰብእ ፡ ፈቃድያን ፡ ዘይፈቅዱ ፡ ኀበ ፡ ፈውስ ፡ ሥጋዊ ፡ ወከማሁ ፡ እንከ ፡ መንፈሳዊኒ ወበከመ ፡ ኢኮኑ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይፈቅዱ ፡ ኪያሁ ፡ ይፍቅድዎ ፡ ዘልፈ ፡ በኵሉ ፡ ደዌ ፡ ወከማሁ ፡ መንፈሳዊኒ ፡ ካዕበ ።

፩ሺ፰፻፲፮ ወዘሰ ፡ ብዙሕ ፡ ለሊቀ ፡ ዘውእቱ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ከመ ፡ ይመስክር ፡ ዲበሁ ፡ ወያንትግ ፡ እምኔሁ ፡ ዝኒ ፡ በአምሳለ ፡ ዘይሬኢ ፡ ዘይከውን ፡ በቍዔተ ፡ በዘመኑ ። ወአእምሮ ፡ ከመ ፡ መፍቅደ ፡ ሕግ ፡ ይትከፈል ፡ ኀበ ፡ ፪ቱ ፡ አክፋል ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ አሚን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ ወካልእኒ ፡ ገቢረ ፡ ዘያሠምሮ ፡

ከዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ በሌላ ፡ የተናገሯቸው ፡ ሌሎች ፡ መፍቅዳትም ፡ አሉ ።

፩ሺ፰፻፲፫ ስለጥቅምስ ፡ ጥበብን ፡ በየወገኑ ፡ ከሚያውቁ ከፈላስፎች ፡ አንዱ ፡ ፈላስፋ ፡ በመገዘር ፡ የፍትወት ፡ ዓባለ ፡ ዘርዕ ፡ ይደክማል ፡ ይቀንሳልም ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ። ይህም ፡ በስምምነት ፡ ከሆነ ፡ በዚች ፡ ቅድስት ፡ ሥርዓት ፡ የተገባ ፡ ነው ።

፩ሺ፰፻፲፬ ኃጢአትን ፡ መታመን ፡ መንፈሳዊ ፡ ፈውስ ፡ ነው ። በመንፈስ ፡ መባሉም ፡ ሥጋዊ ፡ ተዘምዶ ፡ ከሥጋ ፡ ጋር ፡ እንደሚያዛምድ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ ስለሚያዛምድ ፡ ነው ። ሥጋዊ ፡ ፈውስ ፡ ብልህ ፡ ቸር ፡ በሆን ፡ በሐኪም ፡ እጅ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ እንደማይፈጸም ፡ ያለዚያስ ፡ ሰነፍ ፡ ክፉ ፡ በሆነ ፡ ሐኪም ፡ እድናለሁ ፡ ከማለት ፡ መድኃኒት ፡ ማድረጉን ፡ መተው ፡ ይሻላል ። ዳግመኛም ፡ መድኃኒት ፡ የሚያደርጉለት ፡ ድውይ ፡ ይበጅሃል ፡ ከአሉት ፡ ወገን ፡ የሚበጀውን ፡ በመቀበሉ ፡ ነው ። ዳግመኛም ፡ እንደዘመኑ ፡ እንደቦታው ፡ እንደችሎታው ፡ ሁናቴ ፡ በሚቻለው ፡ መድኃኒት ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ ካልሆነስ ፡ ጥቅም ፡ የለውም ፡ መንፈሳዊውም ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ።

፩ሺ፰፻፲፭ መድኃኒት ፡ በዋቂ ፡ ካልተገኘ ፡ ጤንነት ፡ አትመጣም ፡ (አትገኝም) ። እንደዚኹም ፡ የሚሻ ፡ ኃጢአትን ፡ መታመን ፡ በሁለት ፡ ክፍል ፡ ሆነ ፡ በአንዳንድ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በማናቸውም ፡ ዘንድ ፡ አይገኝም ። ከሊቃነ ፡ ጳጳሳቶቻቸው ፡ ወገን ፡ እርሱን ፡ የከለከሉ ፡ በዓለም ፡ አሉ ። በእርሱዋ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ፡ በመልካም ፡ የማይፈጸም ፡ ፫ቱን ፡ ውሳኔዎች ፡ እንደማድረግ ፡ ስለታጣ ፡ ነው ። ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ሥጋዊ ፡ ፈውስን ፡ የሚሹ ፡ ፈቃደኞች ፡ እንዳልሆኑ፡ መንፈሳዊውም ፡ ደግሞ ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ።

፩ሺ፰፻፲፮ ለሊቅ ፡ የሚገባውም ፡ ይኸውም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ነው ፡ በዚህ ፡ ላይ ፡ ሊመሰክር ፡ ከዚህም ፡ ሊያጎድል ፡ ነው ። ይኸውም ፡ በዘመኑ ፡ ጥቅም ፡ የሚሆነውን ፡ በማየቱ ፡ ልክ ነው ። የሕግ ፡ ፈቃድ ፡ ከሁለት ፡ ክፍል ፡ እንደሚከፈል ፡ ዕወቅ ፡ ከእነዚህም ፡ አንዱ ፡ በልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ማመን ፡ ሁለተኛውም ፡ ደስ ፡ የሚያሰ

፩ሺ፫፻፲፯ ወቀዳማዊኒ ፡ ፪ቱ ፡ ክፍል ፡ ዘውእቱ ፡ ጽሒፍ ወውእቱ ፡ ጽሒፈ ፡ ቃል ፡ ወትርጓሜሁ ። ወለዘተጽሕፈሰ ፡ ኢያከውኖ ፡ ለመኑሂ ፡ ከመ ፡ ይወስክ ፡ ዲቤሁ ፡ ወኢከመ ፡ ያንትግ ፡ እምኔሁ ፡ በእንተ ፡ ቃለ ፡ ሐዋርያ ፡ ዘይቤ ፡ "መልአክ ፡ እምሰማይ ፡ ለእመ ፡ መሀረክሙ ፡ ካልአ ፡ እምዘመሀርናክሙ ፡ ንሕነ ፡ ውጉዘ ፡ ለይኩን" ። ወትርጓሜሁስ ፡ ኢይከውኖ ፡ ለመኑሂ ፡ ከመ ፡ ይፈክር ውስቴቱ ፡ ዘይትቃወሞ ፡ ለዘተጽሕፈ ፡ ወኢበዘተጋብኡ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወኢ ፡ ላዕለ ፡ ዘተጽሕፈ ፡ በምክሮሙ፡ ለብዙኃን ፡ እመተርጕማን ፡ ማእምራን ፡ ወቅዱሳን ።

፩ሺ፫፻፲፰ ወዳግምኒ ፡ ኀበ ፡ ፪ቱ ፡ ክፍል ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘሰዉቅ ፡ ውስተ ፡ ዘተጽሕፈ ፡ ዘውእቱ ፡ ቃለ ፡ መጻሕፍት ፡ እምላካውያት ፡ ወጉባኤያት ፡ ውኩፋት ፡ ዘከመ ፡ ጾም ፡ ወጸሎት ፡ ወምጽዋት ፡ ወዘይመስሎ ፡ ለዝንቱ ። ወዝንቱኒ ፡ ይከውን ፡ ከመ ፡ ቀዳማዊ ፡ በዘይትገበር ፡ ቦቱ ፡ ኪያሁ ። ወካልእኒ ፡ ዘኢተግህደ ፡ በመጻሕፍት ፡ እንተ ፡ እመርነ ፡ ኀቤሃ ፡ ወኢኮነ ፡ ከሡተ ፡ ይግበሩ ፡ ባቲ ፡ ወኢተረክበ ፡ ጉባኤ ፡ በእንቲአሃ ፡ አላ ፡ ውእቱሰ ፡ እምግብር ፡ እንተ ፡ ኢዘከርዋ ።

፩ሺ፫፻፲፱ ወለዝንቱ ፡ ባሕቲቱ ፡ ቦቱ ፡ መባሕት ፡ ከመ፡ ይፍታሕ ፡ ወይእስር ፡ ወባሕቱ ፡ ይግበር ፡ በሥርዓተ ፡ ውሳኔ ። ቀዳሚሃኒ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ፍጹመ ፡ ልቡና ፡ በአእምሮ ፡ ጠባይዓዊ ፡ ወረባኃዊ ።

፩ሺ፫፻፳ ወዳግምኒ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ጽሩየ ፡ በሃይማኖቱ፡ ዘየዐቅብ ፡ ቦቱ ፡ ሕገ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘሀሎ ፡ ዲበ ፡ መሠረታቲሁ ፡ ዘዘልፍ ።

፩ሺ፫፻፳፩ ወሣልስ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ምሁረ ፡ በ፪ቱ ፡ አሥራው ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ቃለ ፡ መጻሕፍት ፡ እምላካውያት ፡ ወትርጓሜሆን ፡ ዘየኀብር ፡ ቦቱ ፡ ወዳግም ፡ ዘተጋብኡ ፡ ወኀብሩ ፡ ላዕሌሁ ፡ ማኅበረ ፡ ቅዱሳን ፡ ማእምራን ፡ ወዘኀብሩ ፡ ላዕሌሁ ፡ ካዕበ ፡ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ ስንእዋነ ፡ ላዕለ ፡ ዘኀብሩ ፡ ቦቱ ። ወይለብውዎ ፡ በጥዩቅ ፡ ለዘተናፈቁ ፡ በእንቲአሁ ፡ ወይትአመንዎ ፡ ለዘተሰነአዉ ፡ ላዕሌሁ ።



ኘውን ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ ነው ።

፩ሺ፫፻፲፯ መጀመሪያው ፡ ሁለት ፡ ክፍል ፡ ነው ። ይኸውም ፡ መጻፍ ፡ ነው ። እርሱም ፡ ንባቡንና ፡ ትርጓሜውን ፡ መጻፍ ፡ ነው ። የተጻፈውን ፡ ግን ፡ ለማንም ፡ ቢሆን ፡ በእርሱ ፡ ሊጨምር ፡ ከእርሱም ፡ ሊያጎድል ፡ አይገባውም ። ሐዋርያ ፡ እኛ ፡ ካስተማርናችሁ ፡ ሌላ ፡ መልአክ ፡ ከሰማይ ፡ ቢያስተምራችሁ ፡ የተለየ ፡ ይሁን ፡ ስለ አለ ፡ ነው ። ትርጓሜውም ፡ የተጻፈውን ፡ ወይም ፡ የተባበሩትን ፡ ቅዱሳን ፡ ሀዋቶች ፡ ከሚሆኑ ፡ ከመተርጕማን ፡ ወገን ፡ በብዙዎች ፡ ምክር ፡ የተጻፈውንም ፡ የሚቃወም ፡ አድርጎ ፡ ይተረጉም ፡ ዘንድ ፡ ለማንም ፡ አይገባውም ።

፩ሺ፫፻፲፰ ሁለተኛውም ፡ ሁለት ፡ ክፍል ፡ ነው ፡ ከእነርሱም ፡ አንዱ ፡ በተጻፈው ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ የቅዱሳት ፡ መጻሕፍትና ፡ ተቀባይነት ፡ ያላቸው ፡ የጉባኤያት ፡ ቃል ፡ ነው ። ይኸውም ፡ እንደጾምና ፡ እንደጸሎት ፡ እንደምጽዋትም ፡ ይህንም ፡ እንደመሰለ ፡ ያለ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ በሚሠራበት ፡ ግንዘብ ፡ እንደፊተኛው ፡ ይሆናል ። ሁለተኛውም ፡ በጠቀስነው ፡ መጽሐፍ ፡ ያልተነገረ ፡ ይሠሩበትም ፡ ዘንድ ፡ ግልጥ ፡ ያልሆነ ፡ ነው ። ስለእርሱዋም ፡ ጉባኤ ፡ አልተደረገም ። ከአልጠቀሱዋት ፡ ሥራ ፡ ወገን፡ ነው ፡ እንጂ ።

፩ሺ፫፻፲፱ በዚህ ፡ ብቻ ፡ ሊፈታ ፡ ሊያስር ፡ ሥልጣን ፡ አለው ። ነገር ፡ ግን ፡ በውሳኔ ፡ ደንብ ፡ ያድርግ ፡ መጀመሪያዋም ፡ በጠባይዐዊና ፡ በጠቃሚ ፡ እእምሮ ፡ ፍጹም ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

፩ሺ፫፻፳ ሁለተኛው ፡ በዘለዓለም ፡ መሠረቶቹ ፡ የአለ ፡ የሃይማኖቱን ፡ ሕግ ፡ በሚጠብቅበት ፡ በሃይማኖቱ ፡ የጠራ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

፩ሺ፫፻፳፩ ሦስተኛ ፡ በሁለቱ ፡ መሠረቶቹ ፡ የተማረ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ከእነርሱም ፡ አንዱ ፡ የቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ቃልና ፡ የሚተባበር ፡ ትርጓሜያቸው ፡ ነው ። ሁለተኛም ፡ ቅዱሳን ፡ ሀዋቶች ፡ የሆኑ፡የተባበሩበትና ፡ አንድ ፡ የሆኑበት ፡ ዳግመኛም ፡ በተባበሩበት ፡ ላይ ፡ የተስማሙ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ የተባበሩበት ፡ ነው ። ስለእርሱም ፡ የተለያዩበትን ፡ በጥንቃቄ ፡ ያስተውሉት ፡ የተስማሙበትንም ፡ ይመኑበት ።

አንቀጽ ፡ ፶፩ ።

፩ሺ.፫፻፳፫ ሣልስ ፡ እእምሮተ ፡ አምሳል ፡ ዘያበጽሕ ፡ ኀበ ፡ አግብኦተ ፡ እዕፁቅ ፡ ዘንበር ፡ ላዕሌሃ ፡ ኀበ ፡ ሥርወ ፡ ጕንድ ፡ ዘትትበሃል ፡ ባቲ ፡ ኀበ ፡ ትርጓሜያት ፡ ወጉባኤያት ፡ እንተ ፡ ተሰነአወ ፡ ባቲ ።

፩ሺ.፫፻፳፬ ወራብዕኒ ፡ ትእዛዝ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ማእምረ ፡ በገሃድ ፡ ወልማድ ፡ እምግብረት ።

፩ሺ.፫፻፳፭ ወኃምስ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ትሩፈ ፡ ምግባር ፡ በውስተ ፡ ነፍሱ ፡ ወሥጋሁ ፡ በዘይኩውን ፡ ውኩፈ ፡ ትእዛዘ ፡ ዚአሁ ፡ በኀበ ፡ ሕዝብ ።

፩ሺ.፫፻፳፮ ሳድስ ፡ ከመ ፡ ይርአይ ፡ ዘይሠርዖ ፡ ሎሙ ፡ ዘይትከሀሎሙ ፡ ፀዊሮቱ ፡ በመዋዕሊሁ ፡ ወለዘ ይከውኑ ፡ እሙንቱ ፡ ነዳያን ፡ ላዕሌሁ ፡ እም ሳለ ፡ ዘይረብሖሙ ፡ ትምህርተ ፡ ለባዊተ ፡ ዘይ ጠናቀቁ ፡ ባቲ ፡ ሐልዮታቲሆሙ ፡ ወቀንዮተ ፡ ፈቃዳቲሆሙ ፡ ዘትሜኒ ፡ ባቲ ፡ ገድሎሙ ፡ ወት ትፌጸም ፡ ባቲ ፡ እምልኮቶሙ ፡ ወእንተ ፡ ትደሉ ፡ ለሠናይቶሙ ፡ ወግብረ ፡ ሥርዓቶሙ ፡ ዘትትፌጸም ፡ ባቲ ፡ ሃይማኖቶሙ ፡ ጥዩቀ ፡ ወዘ ይረትዕ ፡ ባቲ ፡ ግብሮሙ ፡ በዓለምሙኒ ፡ ወደ ኃሪቶሙኒ ።

፩ሺ.፫፻፳፯ ወሳብዕ ፡ ከመ ፡ ይትማከር ፡ በዘይፈትሕ ፡ ወየአስር ፡ ምስለ ፡ ማእምራን ፡ ወንጹሓን ፡ እም ካህናቲሁ ፡ ወሕዝቡ ፡ ወመኳንንቲሁ ፡ ወቅሩ ባኒሁ ፡ ዘታሕተ ፡ ሥልጣኑ ፡ በባሕቲቶሙ ፡ ወበተጋብኦ ፡ ወእምድኅረ ፡ ተሰነአወ ፡ ቦቱ ፡ ይጽሐፉ ፡ ተዘክረ ፡ ነገር ፡ ምክንያተ ፡ ዘተጋ ብኡ ፡ በእንቲአሁ ፡ ወተመክንዮተ ፡ በቀኖናት ፡ ዘቦቱ ፡ ወከዊነ ፡ ተሰናእዎ ፡ ዘካህናት ፡ ወመኳ ንንት ፡ ዘላዕሌሁ ። ወለእመኒ ፡ ኮነ ፡ ግብረ ፡ ዐቢየ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይትጋብኡ ፡ በእንቲአሁ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ወዐበይተ ፡ ካህናት ፡ ወመኳ ንንት ፡ ወዘቦቱ ፡ እእምሮ ፡ ወገቢረ ፡ ጽድቅ ። ወይጽሐፉ ፡ ጽሕፈተ ፡ እደዊሆሙ ፡ ላዕለ ፡ ዘተ ጽሕፈ ፡ ወያስልጡ ፡ እምኔሁ ፡ መጻሕፍተ ፡ ወያንብብዎሙ ፡ ውስተ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያ ናት ፡ ቅድመ ፡ ካህናት ፡ ቅድመ ፡ ኩሉ ፡ ውስተ ፡ ብሔር ፡ ወእህጉር ።

፩ሺ.፫፻፳፰ ክፍል ፡ በእንተ ፡ ዘይደሉ ፡ ተእኀዞ ፡ ምስለ ፡

ስለ ፡ ወንበርና ፡ ስለ ፡ ማዘረት ።

፩ሺ.፫፻፳፫ ሦስተኛውም ፡ በእርስዋ ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ትርጓ ሜዎችን ፡ በትርጓሜና ፡ በተሰማሙበት ፡ ጉባኤ ፡ ወደምትነገር ፡ ወደግንድ ፡ ሥር ፡ ወደ መመለስ ፡ የሚያደርስ ፡ ምሳሌን ፡ ማወቅ ፡ ነው ።

፩ሺ.፫፻፳፬ ዐራተኛውም ፡ ትእዛዝ ፡ ከሥራዎች ፡ ወገን ፡ በግልጽና ፡ በልማድ ፡ ዕዋቂ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

፩ሺ.፫፻፳፭ አምስተኛው ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ተቀባይ ፡ በሚሆን ፡ ትንዛዝ ፡ በነፍስና ፡ በሥጋዉ ፡ በሥራ ፡ ፍጹም ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

፩ሺ.፫፻፳፮ ፮ኛ ፡ በዘመኑ ፡ የሚሠራላቸው ፡ ሥርዓት ፡ መሸከሙ ፡ የሚቻላቸው ፡ እንደሆነ ፡ ወይም ፡ እነርሱ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ ችግረኞች ፡ የሚሆኑ ፡ (የማይችሉት) ፡ እንደሆነ ፡ ይመለከት ፡ ዘንድ ፡ ነው ። አሳቦቻቸው ፡ የሚታረሙባት ፡ ፈቃዶ ቻቸው ፡ የሚገዙባት ፡ ገድላቸው ፡ የምትበጅ ባት ፡ አምልኮታቸው ፡ የምትፈጸምበት ፡ ለመ ልካምነታቸውና ፡ ለሥርዓታቸው ፡ ግብር ፡ የም ትገባ ፡ ሃይማኖታቸው ፡ በእርግጥ ፡ ፍጹም ፡ የምትሆንባት ፡ በዓለማቸውና ፡ በመጨረሻቸ ውም ፡ (በኋላኛው) ፡ ሥራቸው ፡ የምትቀናባት፡ ልባዊት ፡ ትምህርትን ፡ እንደሚጠቅማቸው ፡ ነው ።

፩ሺ.፫፻፳፯ ሰባተኛም ፡ ስለሚፈታውና ፡ ስለሚያስ ረው ፡ ከካህናቱ ፡ ወገን ፡ ከዐዋቆችና ፡ ከንጹ ሓን ፡ ከሕዝቡ ፡ ከመኳንንቱ ፡ ከሥልጣኑ ፡ በታች ፡ ካሉ ፡ ከባለሟሎቹም ፡ ጋር ፡ በየብቻ ቸው ፡ በስብሰባም ፡ ይማከር ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ከተስማሙበት ፡ በኋላ ፡ ስለእርሱ ፡ የተሰበሰቡ በትን ፡ የነገሩን ፡ ማስታወሻ ፡ በእርሱ ፡ የሚገ ኘውን ፡ የጥቅሙን ፡ ምክንያት ፡ በእርሱም ፡ ላይ ፡ የካህናቱና ፡ የመኳንንቱን ፡ የስምምነት ፡ ሁኔታ ፡ ይጻፉ ። ነገሩ ፡ ታላቅ ፡ ቢሆን ፡ ስለእ ርሱ ፡ ኤጲስቆጶሳትና ፡ ከካህናት ፡ አለቆች ፡ መኳንንትም ፡ እውቀትና ፡ የእውነት ፡ ሥራ ፡ ያለውም ፡ ሊሰበሰቡ ፡ ይገባል ። በተጻፈውም ፡ ላይ ፡ በእጃቸው ፡ ፊርማ ፡ ይፈርሙ ። (በእጃ ቸው ፡ ጽሕፈት ፡ ይጻፉ) ፡ ከእርሱም ፡ ደብዳቤ ዎችን ፡ ገልብጠው ፡ በካህናቱና ፡ በሁሉ ፡ ፊት ፡ በገጠርና ፡ በከተሞች ፡ በየቤተ ፡ ክርስቲ ያኑ ፡ ያነብቡአቸው ።

፩ሺ.፫፻፳፰ ክፍል ። ፍጻሜው ፡ ከኒቅያ ፡ ጉባኤ ፡ ጋር ፡

ቀኖና ፡ ኒቅያ ፡ ተፍጻሜታ ፡ ወይትኅሠሥ ፡ ዝንቱ ፡ ውስተ ፡ መጻሕፍተ ፡ እግዚእብሔር ፡ ወይጠይቅ ፡ እምሐራ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እስመ ፡ የእምር ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ እዘዘ ፡ እግዚ አብሔር ፡ በእንተዝ ፡ ኵሉ ። ወለእመሰ ፡ ተዐ ደወ ፡ ፩ዱ ፡ ዘእቅደምነ ፡ ነገሮቶ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ተቃወሞ ፡ ለእግዚእብሔር ።

፩ሺ.፰፻፳፰ ወይቤ ፡ እግዚእነ ፡ በወንጌል ፡ "ዘሰ ፡ ኮነ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ይሰምዕ ፡ ነገረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ብፁዕ ፡ ውእቱ ፡ ዘይሰምዕ ፡ ነገረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወየዐቅቦ ። ወይቤ ፡ ለአርዳኢሁ ፡ ዘሰምዐ ፡ እምኔክሙ ፡ ኪያየ ፡ ሰምዐ ፡ ወዘሰበየኒክሙ ፡ አበየኒ" ።

፩ሺ.፰፻፳፱ ወይቤሉ ፡ ሐዋርያትኒ ፡ በውስተ ፡ ተፍጻሜተ ፡ ቀኖናት ፡ ዘኮሉ ፡ ሠወጽነ ፡ ንእዝዘክሙ ፡ ንሕነ ፡ ኦ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ዘንተ ፡ ቀኖና ፡ ወለእመ ፡ ነበርክሙ ፡ ቦቱ ፡ ትትባልሑ ፡ ወትከውን ፡ ሰላም ፡ ለክሙ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ። ወለእመሰ ፡ ኢተወከፍክሙ ፡ ወኢተእዘዝክሙ ፡ ለዘውስቴቱ ፡ ይእዜ ፡ ትከውኑ ፡ ለስላቅ ፡ ወታንብሩ ፡ ኀዘነ ፡ በበይናቲክሙ ፡ ወእምድኅረዝ ፡ ትነሥኡ ፡ ኵነኔ ፡ ዘይደሉ ፡ ለዕልወታቲክሙ ።

፩ሺ.፰፻፴ ወእግዚእብሔር ፡ ባሕቲቱ ፡ ወወልዱ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፈጣሬ ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረታት ፡ ይረሲክሙ ፡ ፩ደ ፡ ሥጋ ፡ ለኵልክሙ ፡ በብዝኀ ፡ ሰላሙ ። ወያስተዳሉ ፡ ለክሙ ፡ ኵሎ ፡ ሠናየ ፡ ከመ ፡ ኢትትመየጡ ፡ ወትኩኑ ፡ ዘእንበለ ፡ ደነስ ፡ ወዘእንበለ ፡ ኃጢአት ። ወይረሲክሙ ፡ ድልዋነ ፡ ለማኅደረ ፡ ሕይወት ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፡ እመንገለ ፡ ወልዱ ፡ ፍቁር ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጣሬ ፡ መድኀኒነ ፡ ዝንቱ ፡ ዘበእንቲአሁ ፡ ምስሌሁ ፡ ስብሐት ፡ ወምስለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፡ ዓለም ፡ አሜን ።



መያያዝ ፡ ስለሚገባ ፡ ይናገራል ። ይህ ፡ ከእግዚ አብሔር ፡ መጻሕፍት ፡ ይመርምር ። ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጭፍሮችም ፡ ይረዳ ። ስለዚህ ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደአዘዘ ፡ ርሱ ፡ ያውቃልና ። አንድ ፡ ሰው ፡ አስቀድመን ፡ የተናገርነውን ፡ ቢያፋልስ ፡ ግን ፡ ርሱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ተቃወመ ፡ እኮ ።

፩ሺ.፰፻፳፰ ጌታችንም ፡ በወንጌል ፡ "ከእግዚአብሔር ፡ የሆነ ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ ይሰማል ፡ አለ ። (ዮሐ ፡ ፰ ፡ ፵፯) ። ዳግመኛም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ ሰምቶ ፡ የሚጠብቀው ፡ ብፁዕ ፡ ነው ፡ አለ ። (ሉቃ ፡ ፲፩ ፡ ፳፰) ። ለደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ እናንተን ፡ የሰማ ፡ እኔን ፡ ሰማ ፡ እናንተንም ፡ እንቢ ፡ ያለ ፡ እኔን ፡ እንቢ ፡ አለ ፡ አለ ። (ሉቃ ፡ ፲ ፡ ፲፮) ።

፩ሺ.፰፻፳፱ ሐዋርያትም ፡ ቍጥርዋ ፡ ፹፯ ፡ በምትሆን ፡ በመጻፋቸው ፡ መጨረሻ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ሆይ ፡ እኛ ፡ ይህን ፡ ትእዛዝ ፡ እናዝዛችኋለን ። በእርሱም ፡ ብትኖሩ ፡ ትድናላችሁ ። እስከ ፡ መጨረሻም ፡ ድረስ ፡ ሰላም ፡ ለእናንተ ፡ ትሆናለች ፡ እሱ ። ባትቀበሉ ፡ ግን ፡ ዛሬም ፡ በውስጡ ፡ ላላችሁበት ፡ ባትታዘዙ ፡ ለመዘባበቻ ፡ ትሆናላችሁ ። እርስ ፡ በእርሳችሁም ፡ ኀዘንን ፡ ታኖራላችሁ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ስወንጀለኛነታችሁ ፡ የሚገባ ፡ ቅጣትን ፡ ትቀበላላችሁ ።

፩ሺ.፰፻፴ ብቻኛው ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጁ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ፍጥረቶችን ፡ ሁሉ ፡ የፈጠረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ በሰላሙ ፡ ብዛት ፡ ሁላችሁን ፡ አንድ ፡ ሥጋ ፡ ያድርጋችሁ ። በጎውንም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ያዘጋጅላችሁ ። እንዳትመለሱ ፡ ያለ ፡ ነውርና ፡ ያለ ፡ ኃጢአት ፡ ትሆኑ ፡ ዘንድ ። እስከ ፡ ዘለዓለሙ ፡ ድረስ ፡ ለሕይወት ፡ ማደሪያ ፡ የበቃችሁ ፡ ያድርጋችሁ ። እርሱ ፡ ፈጣሪ ፡ መድኃኒታችን ፡ እግዚአብሔር ፡ በልጁ ፡ በወዳጁ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በእርሱ ፡ ከእርሱ ፡ ጋራ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ጋራ ፡ እስከ ፡ ዘለዓለሙ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ፡ አሜን ።

## አንቀጸ ተዋርሶ ።

ዘተሰነዐወ ፡ ላዕሌሁ ፡ እግዚእ ፡ አባ ፡ ቄርሎስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእለ ፡ እስክንድርያ ፡ ምስለ ፡ ኤጲስቆጶሳቲሁ ፡ ወሊቃውንቲሁ ፡ ወመኳንንቲሁ

## የመወራረስ አንቀጽ ።

የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ጌታ ፡ አባ ፡ ቄርሎስ ፡ ከኤጲስቆጶሳቱ ፡ ከሊቃውንቱና ፡ ከመኳንንቱ ፡ ጋራ ፡ የተስማሙበት ፡ ነው ።

እንቀጽ ፡ ተዋርሶ ።

፩ሺ፰፻፴፩ ወውእቱ ፡ ፰ቱ ፡ ምዕራፍ ፡ ወመብዝኅቱኒ ፡ እምነ ፡ ዘጸሐፎ ፡ አባ ፡ ቆዝሞስ ፡ ፩ዱ ፡ እምሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእስ ፡ እስክንድርያ ፡ ወይቤ ፡ በተፍጻሜቱ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ እምዘ ፡ ሠርዕዎ ፡ እምሊቃነ ፡ ሕግ ፡ ወተረፈ ፡ ዚእሁ ፡ እምልብ ፡ ወዘልማድ ። ወዝንቱ ፡ ተሠርዐ ፡ እመ ፡ ፲ወ፯ሎ ለወርኀ ፡ መስከረም ፡ በ፱፻፶ወ፰ቱ ፡ ዓመተ ፡ ሰማዕታት ፡ ንጹሓን ፡ ወእምልደተ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በ፲፻ወ፪፻፵ወ፩ዱ ፡ ዓመት። ትንብልናሆሙ፡ ተሀሉ ፡ ምስለ ፡ ኵሎሙ ፡ ክርስቲያን ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

፩ሺ፰፻፴፪ ምዕራፍ ፡ በእንተ ፡ ዘያቀድሙ ፡ ገቢረ ፡ በዘተኀድገ ፡ ለወረስ ። ያቅድሙ ፡ ሜጠ ፡ ግንዘቱ ፡ ወእስተዋፅኦተ ፡ መቃብሩ ፡ ወግብረ ፡ ግንዘቱ ፡ ወእምዝ ፡ ይፍዲ ፡ ዕዳ ፡ ዘሀሎ ፡ ላዕለ ፡ ምዉት ። ወሰእመ ፡ ኮነ ፡ ንዋይ ፡ ዘኀደገ ፡ ኢየአክል ፡ ሰፈድዮ ፡ ልቃሕ ፡ ወራሲኒ ፡ ለእመ ፡ ኢወረሶ ፡ ለንዋይ ፡ ኢይእኅዞ ፡ ፈድዮ ፡ ዕዳ ፡ ዘልቃሕ ። ወእመሰ ፡ ነሥአ ፡ ኪያሁ ፡ ይጽሐፎ ፡ በቅድመ፡ ሰማዕት ፡ ወየሀቦ ፡ ለኵሉ ፡ ለለ ፡ ፩ዱ ፡ እምእብዕልተ ፡ ዕዳ ፡ ወትእዛዛትስ ፡ በከመ ፡ እምጣነ ፡ ንዋዩ ። ወለእመ ፡ መጽአ ፡ ካልእ ፡ ዘሎቱ ፡ ዕዳ ፡ ያማብእ ፡ ክፍሎ ፡ ኀበ ፡ ጥንተ ፡ ርስት ፡ ዘኀደገ ፡ እምንዋይ ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ወራሲሁ ፡ ዘተመጠዎ ፡ ወኢፈለጠ ፡ ኪያሁ ፡ በስምዕ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይፍዲ ፡ ንዋዮሙ ፡ እምድኅረ ፡ አጠየቀ ፡ በስምዕ ፡ ርቱዕ ።

፩ሺ፰፻፴፫ ወእምድኅረ ፡ ውእቱ ፡ እብእተ ፡ ቍርባናት ፡ ዘዕዉቅ ፡ ወብፅዐታት ፡ እምላካውያት ፡ ወእምትእዛዘ ፡ ሕግ ፡ እምላካዊት ፡ በከመ ፡ መንፈቀ ፡ ንዋዩ ፡ ወእመኒ ፡ ራብዕተ ፡ እዴሁ ፡ ሰዘኀደገ ፡ ባሕቲቱ ፡ ወእመ ፡ ኮነ ፡ መንፈቀ ፡ ንዋይ ፡ ርኁቀ ፡ ይከፍልዎ ፡ ለንዋይ ፡ ዘሀሰወ ፡ ወዘርኁቅሂ ፡ ይከፍልዎ ፡ ማእከለ ፡ እሉ ፡ ዘተእዘዘ ፡ ሎሙ ፡ ወማእከለ ፡ ወራሲ ፡ በበክፍሎሙ ። ወለእመ ፡ ኢሀሰወ ፡ በመጽሐፈ ፡ ትእዛዙ ፡ ውሂበ ፡ ምጽዋት ፡ መፍትው ፡ ከመ ፡ ይፍልጡ ፡ እምነ ፡ ዘኀደገ ፡ ምጽዋተ ፡ በሥምረተ ፡ ወራሲ ፡ ወበሥምረቱ ፡ ለዘተእዘዘ ፡ ሎቱ ።

፩ሺ፰፻፴፬ ወኢይትኃሠሥዎሙ ፡ ለሰብእ ፡ ምዉት ፡ በዕዳሁ ፡ ወኢ ፡ በዕዳሆሙ ፡ በምንትኒ ፡ እስከ ፡ ፴ ፡ መዋዕል ።

የመወራረስ ፡ አንቀጽ ።

፩ሺ፰፻፴፩ ይኸውም ፡ ስምንት ፡ ምዕራፍ ፡ ነው ። አብዛኛውም ፡ ከእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ አንዱ ፡ አባ ፡ ቆዝሞስ ፡ ከጻፈው ፡ ነው ። በመጨረሻውም ፡ የሕግ ፡ ሊቃውንት ፡ ከጻፉት ፡ የቀረውም ፡ ከልብና ፡ ከልማድ ፡ የተገኘ ፡ እንደሆነ ፡ ተናገረ ። ይህም ፡ በመስከረም ፡ ወር ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ በ፱፻፶፰ ፡ ንጹሓን ፡ በሆኑ ፡ በሰማዕታት ፡ ዘመን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም በተወለደ ፡ በአንድ ፡ ሺ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ዐርባ ፡ አንድ ፡ ዘመን ፡ ተጻፈ ። ልመናቸው ፡ ከክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ፡ አሜን ።

፩ሺ፰፻፴፪ ምዕራፍ ። ለውርስ ፡ በተወው ፡ ገንዘብ ፡ መሥራትን ፡ በሰሚያስቀድሙ ፡ ይናገራል ። የመግነዙን ፡ ዋጋና ፡ የመቃብሩን ፡ መዋጮ ፡ የመግነዙንም ፡ ሥራ ፡ ያስቀድሙ ። ከዚህ ፡ በኋላም ፡ በሟቹ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ዕዳ ፡ ይከፈል ። የተወው ፡ ገንዘብ ፡ ብድሩን ፡ ለመክፈል ፡ የማይበቃ ፡ ቢሆን ፡ ወራሽም ፡ ገንዘቡን፡ ካልወረሰው ፡ የብድርን ፡ ዕዳ ፡ መክፈል ፡ አይዘውም ። ቢወርሰው ፡ ግን ፡ በምስክር ፡ ፊት ፡ ይጻፈው ። ከባለዕዳዎችም ፡ ለያንዳንዱ ፡ ለሁሉ ይስጠው ። (ትእዛዝ ፡) አከፋፈሉ ፡ ግን ፡ እንደ ገንዘቡ ፡ መጠን ፡ ነው ። ሌላም ፡ ዕዳ ፡ ያለውም ቢመጣ ፡ ከገንዘቡ ፡ ወደተወው ፡ ወደርስቱ ፡ መጀመሪያ ፡ ድርሻውን ፡ ያግባ ። ወራሹም ፡ በምስክር ፡ ያነን ፡ ለይቶ ፡ ያልተቀበለ ፡ ቢሆን ፡ በታመነ ፡ ምስክር ፡ ካረጋገጡ ፡ በኋላ ፡ ገንዘባቸውን ፡ ሊከፍል ፡ ይገባዋል ።

፩ሺ፰፻፴፫ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የታወቀውን ፡ ቍርባንና ፡ እምላካውያት ፡ ብፅዓቶችን ፡ ማስገባት ፡ (መስጠት) ፡ ይገባል ። ከእምላካዊት ፡ ሕግ ፡ ትእዛዝም ፡ የተነሣ ፡ እንደገንዘቡ ፡ እኩሌታ ፤ ከተወውም ፡ ገንዘብ ፡ አራተኛውን ፡ እጅ ፡ ቢሆንም ። የገንዘቡ ፡ እኩሌታ ፡ የራቀ ፡ ቢሆንም ፡ ያለውንና ፡ የራቀውን ፡ ገንዘብ ፡ በታዘዘላቸው ፡ ሰዎችና ፡ በወራሽ ፡ መካከል ፡ በየድርሻቸው ፡ ይከፈሉት ፡ በትእዛዝ ፡ (በኑዛዜ) ፡ ደብዳቤ ፡ ምጽዋት ፡ ስጡል ፡ ባይኖር ፡ ከተወው ፡ ገንዘብ ፡ በወራሽ ፡ ፈቃድና ፡ በታዘዘለት ፡ ሰው ፡ ፈቃድ ፡ ለምጽዋት ፡ ሊለዩ ፡ ይገባል ።

፩ሺ፰፻፴፬ የሟችን ፡ ሰዎች ፡ በእርሱ ፡ ዕዳ ፡ ወይም ፡ በራሳቸው ፡ ዕዳ ፡ እስከ ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ በምንም ፡ አይጠይቋቸው ።

አንቀጽ ፡ ተዋርሶ ፡፡

፩ሺ፰፻፴፭ ምዕራፍ ፡ ዘብእሲት ፡ ምስለ ፡ ወራስያኒ ፡ ምታ ፡፡ ለእመ ፡ ኮኑ ፡ ውሉዳ ፡ ወሶበሂ ፡ ይከውኑ ፡ ፫ተ ፡ ወመትሕተ ፡ ወላቲ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ራብዕተ ፡ እድ ፡፡ ወለእመ ፡ ኮኑ ፡ ፬ተ ፡ ወላዕለ ፡ ወላቲ ፡ ከመ ፡ ዘ፩ዱ ፡ እምውሉዳ ፡፡ ወለእመ ፡ ኮኑ ፡ ዘመዱ ፡ መንፈቁ ፡ ይኩን ፡ ላቲ ፡ ወሎሙኒ ፡ መንፈቀ ፡ ዚአሁ ፡፡ ወእመሰ ፡ አልቦቱ ፡ ወራሲ ፡ ዘይዘመዶ ፡ ይኩን ፡ ላቲ ፡ ኵሉ ፡ ዘኀደገ ፡ ወለምታኒ ፡ ፍትሐ ፡ ዚአሃ ፡፡

፩ሺ፰፻፴፮ ለፈኃሪኒ ፡ ወለፍኅርት ፡ ለእመ ፡ ተዳደቃ ፡ ሞት ፡ ለብእሲትኒ ፡ ያግብእ ፡ ፈኃሪ ፡ አው ፡ ወራስያኒሁ ፡ እምድኅሬሁ ፡ እምንዋየ ፡ ብእሲት ፡ እው ፡ እምስብእ ፡ ዚእሃ ፡ ኵሎ ፡ ዘነሥኡ እምኔሁ ፡ ሕዬ ፡ ወእምኃ ፡ እንበለ ፡ ዘተበልዐ ፡ ወዘተሰትየሂ ፡ ወዘይመስሎ ፡ ለዝንቱ ፡፡ ወለእመ ፡ ሞተ ፡ ብእሲ ፡ እንዘ ፡ አልቦ ፡ ዘይወርሶ ፡ ይኅድጉ ፡ ላቲ ፡ ዘነሥአት ፡ እምኔሁ ፡ አው ፡ ስብእ ፡ ዚእሃ ፡፡ ወእመሰ ፡ ቦቱ ፡ ዘይወርሶ ፡ ታግብእ ፡ ኵሎ ፡ ዘነሥአት ፡ እምኔሁ ፡ ወእመኒ ፡ ስብእ ፡ ዚእሃ ፡ ሕዬ ፡ ባሕቲቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ካልኡ ፡፡

፩ሺ፰፻፴፯ ምዕራፍ ፡ ዘመዓርጋተ ፡ ወራስያን ፡ ቀዳሚ ፡ መዓርግ ፡ ዘውሉድ ፡ ተባዕት ፡ ወአንስት ፡ እለ ፡ እውስቡ ፡ ወእለ ፡ ኢያውስቡ ፡ ይረስዎሙ ፡ በዕሩይ ፡ ለአቡሆሙ ፡ ወለእሞሙ ፡፡ ወእመቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘእዕረፈ ፡ እምቅድመ ፡ ዕረፍተ ፡ ወላድያኒሁ ፡ ወእትረፈ ፡ ውሉደ ፡ ይረሱ ፡ ደቂቁ ፡ ምስለ ፡ እኃወ ፡ እቡሆሙ ፡ ወእኃተ ፡ እቡሆሙ ፡ እምነ ፡ እምኄዎሙ ፡ ወምስለ ፡ እኃወ ፡ እሞሙ ፡ ወእኃተ ፡ እሞሙ ፡ እምነ ፡ እምኄዎሙ ፡ ዘኮነ ፡ አቡሁ ፡ ይወርሶ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ሕያወ ፡ ውእቱ ፡፡ ወእምድኅረ ፡ መዓርገ ፡ ውሉድ ፡ መዓርጎሙ ፡ ለውሉደ ፡ ውሉድ ፡ በበሙራይሙ ፡ መዓርግ ፡ እምድኅረ ፡ መዓርግ ፡ በከመ ፡ ዘከርነ ፡ በመዓርገ ፡ ውሉድ ፡፡

፩ሺ፰፻፴፰ መዓርግ ፡ ዳግሚት ፡ ወለእመ ፡ ኢተረክበ ፡ ፩ዱ ፡ እምነ ፡ ዘርኡ ፡ ለዘእዕረፈ ፡ ይከውን ፡ ኵሉ ፡ ርስተ ፡ ዚአሁ ፡ ለአቡሁ ፡ ወለእሙ ፡ ለአቡሁ ፡ ፪ቱ ፡ ሣልስተ ፡ እድ ፡ ወለእሙ ፡

የመወራረስ ፡ አንቀጽ ፡፡

፩ሺ፰፻፴፭ ምዕራፍ ፡ ሴት ፡ ከባልዋ ፡ ወራሾች ፡ ጋር ፡ ልታደርገው ፡ የሚገባውን ፡ ይናገራል ፡፡ (ወራሾች) ፡ ልጆቿ ፡ ቢሆኑ ፡ ፫ ፡ ወይም ፡ የሚያንሱ ፡ ቢሆኑ ፡ ለእርሱዋም ፡ ከእነርሱ ፡ ጋር ፡ ዐራተኛ፡ እጅ ፡ አላት ፡፡ ፬ ፡ ወይም ፡ የሚበዙ ፡ ቢሆኑ ፡ ለእርስዋም ፡ ከልጆቿ ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ አላት ፡፡ ዘመዶቹም ፡ ቢሆኑ ፡ እኩሌታው ፡ ለእርሱዋ ፡ እኩሌታውም ፡ ለእነርሱ ፡ ይሁን ፡፡ የሚዛመደው ፡ ወራሽ ፡ ባይኖረው ፡ ግን ፡ የተወው ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ ለእርሱዋ ፡ ይሁን ፡፡ ለባልዋም ፡ ለእርሱዋ ፡ የተፈረደው ፡ ነው ፡፡

፩ሺ፰፻፴፮ ለአጨና ፡ ለታጨችም ፡ ሴቷን ፡ ሞት ፡ ድንገት ፡ ቢያገኛት ፡ አጮኛው ፡ ወይም ፡ ከእርሱ ፡ በኋላ ፡ ወራሾቹ ፡ ከተበላና ፡ ከተጠጣ ፡ ይህንም ከሚመስለው ፡ በቀር ፡ ከሴቷ ፡ ገንዘብ ፡ ወይም፡ ከሰዎቿ ፡ ከእርሱ ፡ የተቀበሉትን ፡ ሁሉ ፡ ማጫውንና ፡ እጅ ፡ መንሻውን ፡ ይመልስ ፡ (ይቀበል) ፡፡ ወንድ ፡ ወራሽ ፡ ሳይኖረው ፡ ቢሞት ፡ ከእርሱ ፡ የተቀበለችውን ፡ ወይም ፡ ዘመዶቿ የተቀበሉትን ፡ ይተዉላት ፡፡ ወራሽ ፡ ቢኖረው ፡ ግን ፡ ከእርሱ ፡ የተቀበለችውን ፡ ሁሉ ፡ ሰዎቿም ፡ የተቀበሉትን ፡ ከሌላው ፡ (ከትልወት) ፡ በቀር ፡ ማጫ ፡ ብቻ ፡ ሲቀር ፡ ትመልስ ፡፡

፩ሺ፰፻፴፯ ምዕራፍ ፡ የወራሾችን ፡ መዓርግ ፡ ይናገራል ፡፡ መጀመሪያው ፡ መዓርግ ፡ የልጆች ፡ ነው ፡፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ያገቡና ፡ ያላገቡም ፡ አባታቸውንና ፡ እናታቸውን ፡ በትክክል ፡ ይውረሱአቸው ፡፡ ከወላጆቹም ፡ ሞት ፡ አስቀድሞ ፡ ከእነርሱ ፡ ወገን ፡ የሞተ ፡ ቢኖር ፡ ልጆችንም ፡ ቢያተርፍ ፡ (ቢወልድ) ፡ ከአያታቸው ፡ ከተወለዱ ፡ ከአባታቸው ፡ ወንድሞችና ፡ ከአባታቸው ፡ እኅቶች ፡ ጋራ ፡ ከአያታቸው ፡ ከተወለዱ ፡ ከእናታቸው ፡ ወንድሞችና ፡ ከእናታቸው ፡ እኅቶች ፡ ጋራም ፡ አባታቸው ፡ ደኅና ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ይወርሰው ፡ የነበረውን ፡ ይውረሱ ፡፡ ከልጆችም ፡ መዓርግ ፡ ቀጥሎ ፡ እንደ አወራረዳቸው ፡ የልጅ ፡ ልጆች ፡ መዓርግ ፡ ነው ፡፡ በልጆች ፡ መዓርግ ፡ እንደጠቀስነው ፡ ከመዓርግ ፡ ቀጥሎ ፡ መዓርግ ፡፡

፩ሺ፰፻፴፰ ሁለተኛይቱ ፡ መዓርግ ፡ ከሞተው ፡ ሰው ፡ ዘር ፡ አንዱም ፡ ባይገኝ ፡ ርስቱ ፡ ሁሉ ፡ ለአባቱና ፡ ለእናቱ ፡ ይሆናል ፡፡ ለአባቱ ፡ ከሦስቱ ፡ እጅ ፡ ሁለቱ ፡ ለእናቱም ፡ ከሦስቱ ፡ እጅ ፡

፩ዱ ፡ ሣልስተ ፡ እድ ። ወእመቦ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘሞተ ፡ ይከውን ፡ ክፍሉ ፡ ለውሉዱ ፡ እለ ፡ እሙንቱ ፡ እኃዊሁ ፡ ወእኃቲሁ ፡ ለዘሞተ ።

፩ሺ፰፻፵፱ መዓርግ ፡ ሣልሲት ፡ ወለእመ ፡ እልቦቱ ፡ እብ ፡ ወኢ ፡ እም ፡ ኵሉ ፡ ርስተ ፡ ዚእሁ ፡ ለእኃዊሁ ፡ ወለእኀቲሁ ፡ ለተባዕት ፡ ወለእንስት ፡ በዕሩይ ፡ ፪ቱ ፡ ሣልስተ ፡ እድ ፡ ለእኃዊሁ ፡ ወእኃቲሁ ፡ ዘእምእቡሁ ፡ ወ፩ዱ ፡ ሣልስተ ፡ እድ ፡ ለእኃዊሁ ፡ ወእኃቲሁ ፡ ዘእምእሙ ። ወይኩን ፡ ለእኁሁ ፡ ዘእምአቡሁ ፡ ወእሙ ፡ መንፈቀ ፡ ርስት ፡ ወለእኁሁ ፡ ዘእምእቡሁ ፡ ሣልስተ ፡ እድ ፡ ለባሕቲቱ ፡ ወለእኁሁኒ ፡ ዘእምእሙ ፡ ሳድስተ ፡ እድ ። ወእመቦ ፡ እምእኃው ፡ ዘኖሁ ፡ እዕረፈ ፡ ወኀደገ ፡ ወልደ ፡ ይረስ ፡ ወልዱ ፡ ክፍለ ፡ እቡሁ ፡ ምስለ ፡ እኃወ ፡ እቡሁ ፡ ወእኃተ ፡ እቡሁ ፡ ወርስተ ፡ እሙኒ ፡ ይረስ ፡ ምስለ ፡ እኃወ ፡ እሙ ፡ ወእኃተ ፡ እሙ ። ወፍትሕኒ ፡ ዘበእንተ ፡ ውሉዶሙ ፡ እምድኅሬሆሙ ፡ ይከውን ፡ ከመ ፡ ፍትሖሙ ፡ መዓርግ ፡ እምድኅረ ፡ መዓርግ ፡ በበመትልዎሙ ።

፩ሺ፰፻፶ መዓርግ ፡ ራብዒት ፡ ወለእመ ፡ ኢተረከበ ፡ ፩ዱ ፡ እምእኃዊሁ ፡ ወእኃቲሁ ፡ ወዘርእሙ ፡ ይኩን ፡ ኵሉ ፡ ርስቱ ፡ ዘኀደገ ፡ ፪ቱ ፡ እድ ፡ ለእምኄው ፡ ወለእምኄውቱ ፡ ዘእቡሁ ፡ በዕሩይ ፡ ወ፩ዱ ፡ ሣልስተ ፡ እድ ፡ ለእምኄዉ ፡ ወእምኄውቱ ፡ ዘእምእሙ ፡ በዕሩይ ። ወይከፍሉ ፡ ርስቶ ፡ ዘኀደገ ፡ ኀበ ፡ ፱ቱ ፡ ክፍል ፡ ፮ቱ ፡ ክፍል ፡ ለእምኄዉ ፡ ወለእምኄዉቱ ፡ ዘእቡሁ ፡ እው ፡ ለ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ሶበ ፡ ይትኃጣእ ፡ ካልኡ ፡ ምስለ ፡ ዘርኡ ፡ ወ፫ቱ ፡ ለእምኄዉ ፡ ወለእምኄዉቱ ፡ ዘእምእሙ ። ወእመቦ ፡ እምነ ፡ እምኄዋት ፡ ዘእዕረፈ ፡ ይኩን ፡ ክፍሉ ፡ ለደቂቁ ፡ ምስለ ፡ እለ ፡ ተርፉ ፡ እምኄዋት ።

፩ሺ፰፻፶፩ መዓርግ ፡ ኃምሲት ፡ ወለእመ ፡ ኢተረከበ ፡ ፩ዱ ፡ እምነ ፡ እምኄዋት ፡ ፬ቱ ፡ ለእለ ፡ ዘከርነ ፡ ለእኃወ ፡ እቡሁ ፡ ወለእኃተ ፡ እቡሁ ፡ ፪ቱ ፡

እንዱ ፡ እጅ ፡ ይገባል ። ከእነርሱም ፡ የሞተ ፡ ቢኖር ፡ ድርሻው ፡ ለልጆቹ ፡ ይሆናል ። እነዚህም ፡ የሞተው ፡ ሰው ፡ ወንድሞቹና ፡ እኅቶቹ ፡ ናቸው ።

፩ሺ፰፻፵፱ ሦስተኛዪቱ ፡ መዓርግ ፡ እባት ፡ ወይም ፡ እናት ፡ ባይኖረው ፡ ርስቱ ፡ ሁሉ ፡ ለወንድሞቹና ፡ ለእኅቶቹ ፡ ለወንዶችም ፡ ለሴቶችም ፡ በትክክል ፡ ይሁን ። ከሦስት ፡ እጁ ፡ ሁለቱ ፡ በአባቱ ፡ ወገን ፡ ላሉ ፡ ወንድሞቹና ፡ እኅቶቹ ፡ ከሦስት ፡ እጁም ፡ አንዱ ፡ በእናቱ ፡ ወገን ፡ ለአሉ ፡ ወንድሞቹና ፡ እኅቶቹ ፡ ይገባል ። በአባቱና ፡ በእናቱ ፡ ወገን ፡ ለአለ ፡ ወንድሙም ፡ የርስት ፡ እኩሌታ ፡ በአባቱ ፡ ወገን ፡ ለሆነ ፡ ወንድሙም ፡ ሦስተኛ ፡ እጅ ፡ ብቻ ፡ በእናቱ ፡ ወገን ፡ ለሆነ ፡ ወንድሙም ፡ ስድስተኛ ፡ እጅ ፡ ከስድስት ፡ አንድ) ፡ ይገባል ። እነሆ ፡ ከወንድሞች ፡ የሞተ ፡ ቢኖር ፡ ልጅም ፡ ቢተው ፡ ልጁ ፡ የአባቱን ፡ ድርሻ ፡ ከአባቱ ፡ ወንድሞችና ፡ ከአባቱ ፡ እኅቶች ፡ ጋራ ፡ ይውረስ ። የእናቱንም ፡ ርስት ፡ ከእናቱ ፡ ወንድሞችና ፡ ከእናቱ ፡ እኅቶች ፡ ጋር ፡ ይውረስ ። ከእነርሱም ፡ በኋላ ፡ ስለ፡ ልጆቻቸው ፡ የሚሆነው ፡ ፍርድ ፡ እንደ ፡ ፍርዳቸው ፡ (እንደ ፡ አባቶች ፡ ፍርድ) ፡ ይሆናል ። ከመዓርግ ፡ ቀጥሎ ፡ መዓርግ ፡ እንደአከታተላቸው ።

፩ሺ፰፻፶ ዐራተኛዪቱ ፡ መዓርግ ፡ ከወንድሞቹና ፡ ከእኅቶቹ ፡ ከዘሮቹም ፡ እንዱ ፡ ባይገኝ ፡ የተወው ፡ ርስቱ ፡ ሁሉ ፡ ሁለቱ ፡ እጅ ፡ በአባቱ ፡ ወገን ፡ ለአሉ ፡ ለወንድ ፡ አያቱና ፡ ለሴት ፡ አያቱ ፡ በትክክል ፡ ከሦስት ፡ እጁ ፡ እንዱም ፡ በእናት ፡ ወገን ፡ ለአሉ ፡ ለወንድ ፡ አያቱና ፡ ለሴት ፡ አያቱ ፡ በትክክል ፡ ይሁን ። የተወውን ፡ ርስቱን ፡ ከዘጠኝ ፡ ክፍል ፡ ይከፈሉት ። ስድስቱ ፡ ክፍል ፡ በአባቱ ፡ ወገን ፡ ለአሉ ፡ ለወንድ ፡ አያቱና ፡ ለሴት ፡ አያቱ ፡ ወይም ፡ ሁለተኛው ፡ ከልጁ ፡ ጋራ ፡ ቢታጣ ፡ ከእነርሱ ፡ ለአንዱ ፡ ይገባል ። ሦስቱም ፡ (ዕጣ) ፡ በእናቱ ፡ ወገን ፡ ለአሉ ለወንድ ፡ አያቱና ፡ ለሴት ፡ አያቱ ፡ ይገባል ። ከአያቶች ፡ ወገን ፡ የሞተ ፡ ቢኖር ፡ ድርሻው ፡ ከቀሩት ፡ አያቶች ፡ ጋር ፡ ለልጆቹ ፡ ይሁን ።

፩ሺ፰፻፶፩ አምስተኛዪቱ ፡ መዓርግ ፡ ከተናገርናቸው ፡ ከአራቱ ፡ አያቶች ፡ አንዱ ፡ ባይገኝ ፡ ከሦስቱ ፡ እጅ ፡ ሁለቱ ፡ በትክክል ፡ ለአባቱ ፡ ወንድሞ

### አንቀጽ ፡ ተዋርሶ ።

ማልስተ ፡ እድ ፡ በዕሩይ ፡ ወለእኃወ ፡ እሙ ፡ ወእኃተ ፡ እሙ ፡ ማልስተ ፡ እድ ፡ በዕሩይ ፡ ወይክፍሉ ፡ ዘኀደገ ፡ ኀበ ፡ ፪ቱ ፡ ክፍል ፡ በከመ ፡ አቅደምነ ፡ ሥሪዐ ። ወናሁ ፡ ዘከርነ ፡ ፍትሐ ፡ እኃው ፡ ዘ፩ዱ ፡ አብ ፡ ወእሐቲ ፡ እም ፡ ምስለ ፡ እኃው ፡ እለ ፡ ኢኮኑ ፡ እም፩ዱ ፡ እብ ፡ ወእሐቲ ፡ እም ፡ በውስተ ፡ እንቀጸ ፡ እኃው ። ወለዘሂ ፡ አዕረፈ ፡ እምኔሆሙ ፡ ወቦቱ ፡ ወልድ ፡ ይረስ ፡ ወልዱ ፡ ዘኮነ ፡ ይወርሶ ፡ አቡሁ ፡ እመ ፡ ሕያው ፡ ውእቱ ፡ ወከማሁ ፡ ፍትሐ ፡ እዝርእቲሆሙ ፡ እምድኅሬሆሙ ፡ መዓርግ ፡ ድኅረ ፡ መዓርግ ፡ በበመትልዎሙ ።

፩ሺ፰፻፺፪ መዓርግ ፡ ሳድሲት ፡ እበወ ፡ እምኄዋን ፡ ወእምኄዋት ፡ ወኍልቆሙ ፡ ፰ቱ ፡ ወእመ ፡ ኢተረክበ ፡ ፩ዱ ፡ እምእለ ፡ ዘከርነ ፡ በመዓርግ ፡ ኃምሲት ፡ ፪ቱ ፡ ማልስተ ፡ እድ ፡ ይኩን ፡ ለወላድያነ ፡ እምኄው ፡ ወወላድያነ ፡ እምኄውት ፡ ዘእምእብ ፡ በዕሩይ ፡ ወለኵሉ ፡ ለለ፩ዱ ፡ እምእበዊሆሙ ፡ ለእምኄዋት ፡ ዘእመንገለ ፡ እብ ፡ ፪ቱ ፡ ክፍል ። ወለለ፩ዱ ፡ እምወላድያነ ፡ እምኄዋት ፡ ዘእመንገለ ፡ እም ፡ ፩ዱ ፡ ክፍል ። ወለዘሂ ፡ አእረፈ ፡ እምኔሆሙ ፡ ይረስ ፡ ወልዱ ፡ ክፍለ ፡ ዚእሁ ፡ ምስለ ፡ እለ ፡ ተርፉ ፡ ወከማሁ ፡ ፍትሐ ፡ እዝርእቲሆሙ ፡ እምድኅሬሆሙ ፡ መዓርግ ፡ እምድኅረ ፡ መዓርግ ፡ በበመትልዎሙ ።

፩ሺ፰፻፺፫ መዓርግ ፡ ሳብዒት ፡ ወለእመ ፡ ኢተረከበ ፡ ፩ዱኒ ፡ እምዝኩራን ፡ ፪ቱ ፡ እድ ፡ ሥልስ ፡ ለውሉደ ፡ እኃወ ፡ እብ ፡ ወለውሉደ ፡ እኃተ ፡ እብ ፡ ወ፩ዱ ፡ ሥልስ ፡ ለውሉደ ፡ እኃወ ፡ እም ፡ ወለውሉደ ፡ እኃተ ፡ እም ፡ በከመ ፡ ተሠርዐ ፡ በእንተ ፡ እኃወ ፡ አቡሁ ። ወዘኮነ ፡ አዕረፈ ፡ እምኔሆሙ ፡ ይረስ ፡ ወልዱ ፡ ክፍሎ ፡ ምስለ ፡ እለ ፡ ተርፉ ፡ ወከማሁ ፡ ፍትሐ ፡ እዝርእቲሆሙ ፡ እምድኅሬሆሙ ፡ ርስት ፡ እምድኅረ ፡ ርስት ፡ እምዘይቴሐት ።

፩ሺ፰፻፺፬ መዓርግ ፡ ሳምኒት ፡ ወእምድኅሬሆሙ ፡ ለእለ ፡ ዘከርነ ፡ ይረሱ ፡ እምኄዋነ ፡ እምኄዋን ፡ ወኍልቆሙ ፡ ፲ወ፮ቱ ፡ ነፍስ ፡ ፪ቱ ፡ ማልስተ ፡ እድ ፡

### የመወራረስ ፡ አንቀጽ ።

ችና ፡ ለእባቱ ፡ እኅቶች ፡ ይገባል ። ለእናቱ ፡ ወንድሞችና ፡ ለእናቱ ፡ እኅቶችም ፡ ሦስተኛው ፡ እጅ ፡ በትክክል ፡ ይገባል ። የተወውንም ፡ ገንዘብ ፡ ሥርዓትን ፡ እንደ ፡ አስቀደምን ፡ ከዘጠኝ ፡ ክፍል ፡ ይከፈሉት ። ከአንድ ፡ እባትና ፡ ከአንዲት ፡ እናት ፡ የተወለዱ ፡ የወንድሞችን ፡ ፍርድ ከአንድ ፡ እባትና ፡ ከእንዲት ፡ እናት ፡ ካልተወለዱ ፡ ወንድሞች ፡ ጋራ ፡ በወንድሞች ፡ አንቀጽ ፡ እነሆ ፡ ተናገርን ። ከእነርሱም ፡ ለሞተው ሰው ፡ ልጅ ፡ ቢኖረው ፡ እባቱ ፡ ደኅና ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ይወርሰው ፡ የነበረውን ፡ ገንዘብ ፡ ይውረሰው ። ከእነርሱም ፡ በኋላ ፡ የልጆቻቸው ፡ ፍርድ ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። እንደ ፡ አከታተላቸው ፡ ከመዓርግ ፡ ቀጥሎ ፡ መዓርግ ።

፩ሺ፰፻፺፪ ለድስተኛዪቱ ፡ መዓርግ ፡ የወንድ ፡ እያቶችና ፡ የሴት ፡ እያቶች ፡ አባቶች ፡ ቍጥራቸውም ስምንት ፡ ነው ። በእምስተኛይቱ ፡ መዓርግ ፡ ከተናገርናቸው ፡ እንዱ ፡ ባይገኝ ፡ ከሦስት ፡ እጁ ፡ ሁለቱ ፡ በእባት ፡ ወገን ፡ ለእሉ ፡ ለወንድ ፡ እያት ፡ ወላጆችና ፡ ለሴት ፡ እያት ፡ ወላጆች ፡ በትክክል ፡ ይሁን ። በአባት ፡ ወገን ፡ ላሉ ፡ ለሴት ፡ እያቶች ፡ ወላጆች ፡ ለእያንዳንዳቸው ፡ ሁሉ ፡ ሁለት ፡ ክፍል ፡ በእናት ፡ ላሉ ፡ ለሴት ፡ እያቶች ፡ ወላጆች ፤ ወላጆችም ፡ ለያንዳንዱ ፡ እንድ ፡ ክፍል ፡ ይገባል ። ከእነርሱም ፡ የሞተውን ፡ ሰው ፡ የርሱን ፡ ክፍል ፡ (ድርሻ) ፡ ልጁ ፡ ከቀሩት ፡ ጋር ፡ ይውረስ ። ከእነርሱም ፡ በኋላ ፡ የልጆቻቸው ፡ ፍርድ ፡ እንደዚህ ፡ ነው ። እንደ ፡ አወራረዳቸው ፡ ከመዓርግ ፡ ቀጥሎ ፡ መዓርግ ።

፩ሺ፰፻፺፫ ሰባተኛዪቱ ፡ መዓርግ ፡ ከተጠቀሱት ፡ ሰዎች አንዱ ፡ ስንኳ ፡ ባይገኝ ፡ ሁለት ፡ ሦስተኛው ፡ እጅ ፡ ለእባት ፡ የወንድሞች ፡ ልጆችና ፡ ለእናት ፡ የእኅቶች ፡ ልጆች ፡ ይገባል ። እንድ ፡ ሦስተኛውም ፡ ለእናት ፡ የወንድሞች ፡ ልጆችና ፡ ለእናት ፡ የእቶች ፡ ልጆች ፡ ይገባል ። ስለ ፡ አባቱ ፡ ወንድሞች ፡ እንደተጻፈ ። ከእነርሱም ፡ የሞተ ፡ ቢኖር ፡ ልጁ ፡ ከቀሩት ፡ ጋራ ፡ ድርሻውን ፡ ይውረስ ። ከእነርሱም ፡ ቀጥሎ ፡ የልጆቻቸው ፡ ፍርድ ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ፡ ከዝቅተኛው ፡ ጀምሮ ፡ ከውርስ ፡ ቀጥሎ ፡ ይውረስ ።

፩ሺ፰፻፺፬ ስምንተኛዪቱ ፡ መዓርግ ፡ ከተናገርናቸው ፡ ሰዎች ፡ በኋላ ፡ የወንድ ፡ እያቶች ፡ ወንድ ፡ እያቶች ፡ ይውረሱ ። ቍጥራቸውም ፡ እሥራ ፡ ስድ

አንቀጽ ፡ ተዋርሶ ።

ለዘመደ ፡ እም ። ወእመቦ ፡ ዘተኀጥአ ፡ እምኔ ሆሙ ፡ ወቦቱ ፡ ወልድ ፡ ይቁም ፡ ወልዱ ፡ በምቅዋመ ፡ ዚአሁ ።

፩ሺ፰፻፵፭ መዓርግ ፡ ታስዕት ፡ ለአኃወ ፡ እብ ፡ ወአኃተ ፡ አበ ፡ እምኔሆሙ ፡ ወእምኔውቱ ፡ ዘእቡሁ ፡ ፪ቱ ፡ ሣልስተ ፡ እድ ፡ ለአኃወ ፡ እም ፡ ወአኃተ ፡ እመ ፡ እምኔው ፡ ወእምኔውቱ ፡ ዘእምእሙ ፡ ፩ዱ ፡ ሣልስተ ፡ እድ ። ወዘተኃጥአ ፡ እምኔሆሙ ይንሣእ ፡ ወልዱ ፡ ከፍለ ፡ ዚአሁ ፡ ወውሉዶሙ ፡ እምድኅሬሆሙ ፡ ከማሆሙ ፡ መዓርግ ፡ እም ድኅረ ፡ መዓርግ ።

፩ሺ፰፻፵፮ ወፈድፋደሰ ፡ ዝንቱ ፡ ተዋርሶ ፡ ሥሩዕ ፡ ተዋርሶ ፡ ዘመድ ፡ እምድኅረ ፡ ዘመድ ፡ ወፈሊጠ ፡ አብ ፡ ወንገዱ ፡ እምነ ፡ እም ፡ ወንገዳ ፡ እስመ ፡ ነገደ ፡ አብ ፡ ይሰመይ ፡ ዘሪኤ ፡ ወአንባሬ ፡ ማኅፀንት ፡ ወነገደ ፡ እም ፡ ከመ ፡ ምድር ፡ ወመዳይ ፡ ወኵሉ ፡ መዓርግ ፡ ኢትረስ ፡ ምስሌሃ ፡ መዓርገ ፡ እንተ ፡ ድኅሬሃ ፡ ዘእንበለ ፡ ወልዱ ፡ ለዘሞተ ፡ ውእቱ ፡ ህየንቴሁ ።

፩ሺ፰፻፵፯ ወለእመ ፡ ኢተረከበ ፡ በመዓርግ ፡ ዘእንበለ ፡ ፩ዱ ፡ ባሕቲቱ ፡ ይረስ ፡ ውእቱ ፡ ኵሎ ፡ ዘባቲ ፡ ወዘተረከበሂ ፡ በመዓርግ ፡ ዘነገደ ፡ እብ ፡ ወነገደ ፡ እም ፡ ይኩን ፡ ለነገደ ፡ እብ ፡ ዘእብ ፡ ወውእቱ ፡ ሣልስተ ፡ እድ ፡ ፪ቱ ፡ ወለነገደ ፡ እም ፡ ዘእም ፡ ወውእቱ ፡ ሣልስተ ፡ እድ ፡ ፩ዱ ፡ ወተባዕትሂ ፡ ምስለ ፡ አንስት ፡ በዕሩይ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ነገድ ፡ እስመ ፡ ተዛምዶቶሙ ፡ ምስለ ፡ ምዉት ፡ እሐቲ ፡ ትዝምድ ።

፩ሺ፰፻፵፰ ወሶበ ፡ ይትፈለጡ ፡ እዝማደ ፡ እቡሁ ፡ ወእሙ ፡ ወትዝምድና ፡ ምስለ ፡ አኃዊሁ ፡ በእንተ ፡ ዘኮኑ ፡ ፩ደ ፡ ዘርአ ፡ ዘእቡሁ ፡ ወ፩ደ ፡ ዘርአ ፡ ዘእሙ ፡ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ይፈልጥዎ ፡ ለ፩ዱ ፡ እምነ ፡ ካልኡ ፡ ወይከውኑ ፡ ከማሆሙ ፡ እለ ፡ እምድኅሬሆሙ ።

፩ሺ፰፻፵፱ ወለዘሂ ፡ እዕረፈ ፡ እቡሁ ፡ ይወርስ ፡ ወልዱ ፡

የመወራረስ ፡ አንቀጽ ።

ሴት ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ። ሁለት ፡ ሦስተኛው ፡ እጅ ፡ ለአባት ፡ ዘመድ ፡ አንድ ፡ ሦስተኛውም ፡ እጅ ፡ ለእናት ፡ ዘመድ ፡ ይገባል ። ከእነርሱም ፡ የሞተ ፡ ቢኖር ፡ ልጅም ፡ ቢኖረው ፡ ልጅ ፡ በአባቱ ፡ ደረጃ ፡ ይተካ ።

፩ሺ፰፻፵፭ ዘጠኝኛዩቱ ፡ መዓርግ ፡ ለአባት ፡ ወንድሞችና ፡ ለወንድ ፡ አያት ፡ አባት ፡ እኅቶች ፡ በአባቱ ፡ በኩል ፡ ላሉ ፡ ሴት ፡ አያቱም ፡ ሁለት ፡ ሦስተኛው ፡ እጅ ፡ ይገባል ። ለእናት ፡ ወንድሞችና ፡ ለወንድ ፡ አያት ፡ እናት ፡ እኅቶች ፡ በእናቱ ፡ በኩል ፡ ላሉ ፡ ለሴት ፡ እያቱም ፡ አንድ ፡ ሦስተኛው ፡ እጅ ፡ ይገባል ። ከእነርሱም ፡ የሞተ ፡ ልጁ ፡ የእርሱን ፡ ድርሻ ፡ ይውሰድ ፡ ከእነርሱ ፡ ቀጥሎ ፡ ልጆቻቸው ፡ እንደ አነርሱ ፡ ከመዓርግ ፡ ቀጥሎ ፡ መዓርግ ።

፩ሺ፰፻፵፮ ይልቁንም ፡ ይህ ፡ መወራረስ ፡ ከዘመድ ፡ በኋላ ፡ የዘመድ ፡ መወራረስ ፡ አባትንና ፡ ወገኖቹንም ፡ ከእናትና ፡ ከወገኖቿ ፡ መለየት ፡ (ማብለጥ) ፡ የታዘዘ ፡ ነው ። የአባት ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ዘሪና ፡ እንደ ፡ እደራ ፡ አስቀማጭ ፡ ይባላልና ፡ የእናት ፡ ወገንም ፡ እንደ ፡ ምድርና ፡ እንደ ፡ ሣጥን ፡ ናት ። መዓርግ ፡ ሁሉ ፡ ወደኋላዋ ፡ ያለውን ፡ መዓርግ ፡ አብራ ፡ አትውረስ ፡ ስለእርሱ ፡ (ስለእባቱ) ፡ ፈንታ ፡ ከሚኘ ፡ ልጅ ፡ በቀር ።

፩ሺ፰፻፵፯ በመዓርግ ፡ (በውርስ) ፡ ጊዜ ፡ ከአንዱ ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ ባይገኝ ፡ ያለባትን ፡ ሁሉ ፡ ያው ፡ ይውረስ ። በመዓርግ ፡ (በአወራረስ) ፡ ጊዜ ፡ የተገኘ ፡ የአባት ፡ ወገንና ፡ የእናት ፡ ወገን ፡ የአባት ፡ ገንዘብ ፡ ለአለባት ፡ ወገን ፡ ይገባል ። ይኸውም ፡ ሁለት ፡ ሦስተኛው ፡ እጅ ፡ ነው ። የእናትም ፡ ገንዘብ ፡ ለእናት ፡ ወገን ፡ ይገባል ። ይኸውም ፡ እንድ ፡ ሦስተኛው ፡ እጅ ፡ ነው ። ወንዶችም ፡ በነገዱ ፡ ሁሉ ፡ ከሴቶች ፡ ጋራ ፡ በትክክል ። ከሚቹ ፡ ጋራ ፡ ተዘምዶአቸው ፡ አንዲት ፡ ተዘምዶ ፡ ናትና ።

፩ሺ፰፻፵፰ የአባቱና ፡ የእናቱ ፡ ዘመዶች ፡ ከወንድሞቹም ፡ ጋራ ፡ ያለ ፡ ዝምድና ፡ ቢለያዩ ፡ የአባቱ ፡ ዘር ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ የእናቱም ፡ ዘር ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ስለሆኑ ፡ ነው ። አንዱንም ፡ ከሌላው ፡ የሚለዩት ፡ ከሆነ ፡ ከአነርሱም ፡ በኋላ ፡ ያሉት ፡ እንደ ፡ እነርሱ ፡ ይሆናሉ ።

፩ሺ፰፻፵፱ አባቱ ፡ የሞተበትም ፡ ልጁ ፡ የአባቱን ፡

ክፍለ ፡ አቡሁ ፡ በከመ ፡ ምግኔ ፡ ሕይወቱ ፡ በከመ ፡ አዘዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ በውስተ ፡ ኦሪት ።

፩ሺ፰፻፶ ወለዘአልቦቱ ፡ ወራሲ ፡ ይኩን ፡ ርስቱ ፡ ዘኀደገ ፡ ለመዛግብተ ፡ ንዋየ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወለእለ ፡ ሀለዉ ፡ ባቲ ፡ እምእግብርት ፡ ያግዕዝዎሙ ።

፩ሺ፰፻፶፩ ወለዘተወልደሂ ፡ በተዋስቦ ፡ ዘሕግ ፡ እምድኅረ ፡ ጸሒፈ ፡ ትእዛዝ ፡ ይረስ ፡ ምስለ ፡ ውሉድ ፡ ቀዳማውያን ፡ ወይኩን ፡ ከመ ፡ ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ።

፩ሺ፰፻፶፪ ሥርዋጽ ፡ ዝንቱ ፡ ሥርዓት ፡ ጠባይዓዊ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ውሉድ ፡ ወዘርእሙ ፡ ይወርስዎሙ ፡ ለአበዊሆሙ ፡ እለ ፡ ሞቱ ፡ ወለእመ ፡ ተኀጥአ ፡ ዘርኦሙ ፡ ይረሱ ፡ አበወ ፡ ምውታን ፡ ወያቂቆሙኒ ፡ እምድኅሬሆሙ ፡ ወውእቶሙኒ ፡ እኀዊሁ ፡ ለዘእዕረፈ ። ወለእመ ፡ ተኀጥኡ ፡ ዘርኦሙ ፡ ይረሱ ፡ እበወ ፡ አበዊሆሙ ፡ ወእምዝ ፡ ውሉዶሙ ፡ እምድኅሬሆሙ ፡ ዘውእቶሙ ፡ አኀወ ፡ አበዊሆሙ ፡ ወአኀወ ፡ እሞሙ ፡ ለእበው ። ወለኵሉ ፡ ዘተፈጸመ ፡ ዘርአ ፡ መዓርጉ ፡ ይወርስዎ ፡ አበወ ፡ አበዊሁ ፡ ወእምዝ ፡ ያቂቆሙ ፡ እምድኅሬሆሙ ፡ ወውእቶሙ ፡ አኀወ ፡ አበው ፡ ወአኀተ ፡ አበወ ፡ እበው ። ወለኵሉ ፡ ዘተፈጸመ ፡ ዘርኡ ፡ ይረሱ ፡ አበወ ፡ እምኄዎን ፡ ወእምዝ ፡ ውሉዶሙ ፡ እምድኅሬሆሙ ፡ አስመ ፡ ዝንቱ ፡ ፍትሑ ፡ ለሞት ጠባይዓዊ ፡ ወውእቱ ፡ ሞተ ፡ እበው ፡ እምቅድመ ፡ ሞተ ፡ ውሉዶሙ ።

፩ሺ፰፻፶፫ ምዕራፍ ፡ በእንተ ፡ ርስተ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ወመነኰሳት ፡ ለይኩን ፡ ንዋየ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዕዉቀ ፡ ወፍሉጠ ፡ እምንዋየ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ከመ ፡ ይትዐቀብ ፡ ንዋዩ ፡ ለወራስያኒሁ ፡ ወያውርሶ ፡ ለዘፈቀደ ፡ ወይትዐቀብ ፡ ዘቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ። ወዙሉ ፡ ዘአጥረየ ፡ በምክንያተ ፡ ኤጲስቆጶስናሁ ፡ ይኩን ፡ ውእቱ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወኢይደልዎ ፡ ከመ ፡ የአዝዝ ፡ ቦቱ ፡ ወኢከመ ፡ ይረሱ ስብእ ፡ ዚአሁ ። ወኵሉ ፡ ዘአጥረየ ፡ እምቅድመ ኤጲስቆጶስናሁ ፡ አው ፡ ተራብኀ ፡ እምዘኮነ ፡ ሎቱ ፡ ወአኮ ፡ በምክንያተ ፡ ኤጲስቆጶስና ፡



ድርሻ ፡ እንደ ፡ ዕድሜው ፡ ይውረስ ። እግዚአብሔር ፡ በኦሪት ፡ እንደ ፡ አዘዘ ። (ዘኍ ፡ ፴፮ ፡ ፮ - ፲፫) ።

፩ሺ፰፻፶ ወራሽ ፡ የሌለውም ፡ ሰው ፡ የተወው ፡ ርስቱ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዕቃ ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ይሁን ። ከባሮችም ፡ ውስጥ ፡ በእርሱዋ ፡ ያሉትን ፡ ነፃ ፡ ያውጧቸው ።

፩ሺ፰፻፶፩ ከትእዛዝ ፡ መጻፍ ፡ በኋላ ፡ በሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ የተወለደም ፡ ከቀደሙት ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ ይውረስ ። ከእነርሱም ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ይሁን ።

፩ሺ፰፻፶፪ ሥርዋጽ ። ልጆችና ፡ የልጅ ፡ ልጆቻቸው ፡ የሞቱ ፡ አባቶቻቸውን ፡ እንደሚወርሱ ፡ ይህ ሥርዓት ፡ የተለመደ ፡ ነው ። ዘርዓቸውም ፡ (ልጃቸውም) ፡ ቢታጣ ፡ የሙታን ፡ አባቶች ፡ ይውረሱ ። ከእነርሱም ፡ ቀጥለው ፡ ልጆቻቸው። እነርሱም ፡ የሟች ፡ ወንድሞቹ ፡ ናቸው ። ዘሮቻቸውም ፡ ቢታጡ ፡ የአባቶቻቸው ፡ አባቶች ፡ ይውረሱ ። ቀጥለውም ፡ ከእነርሱ ፡ በኋላ ፡ ልጆቻቸው ፡ እነርሱም ፡ የእባቶቻቸው ፡ ወንድሞችና ፡ የእናታቸው ፡ ወንድሞች ፡ ናቸው ። የመዓርጉ ፡ ዘርዕ ፡ (የመዓርጉ ፡ ወራሽ) ፡ የአለቀበትን ፡ ሁሉ ፡ የእባቶቹ ፡ አባቶች ፡ (እያቶቹ) ፡ ይወርሱታል ። ቀጥለውም ፡ ከእነርሱ ፡ በኋላ ፡ ልጆቻቸው ፡ እነርሱም ፡ የአባቶች ፡ ወንድሞችና ፡ የእባቶች ፡ አባቶች ፡ እኅቶች ፡ ናቸው ። ዘሩ ፡ ያለቀበትንም ፡ ሁሉ ፡ የወንድ ፡ እያቶች ፡ አባቶች ፡ ይውረሱ ። ቀጥለውም ፡ ከእነርሱ ፡ በኋላ ፡ ልጆቻቸው ፡ የባሕርያዊ ፡ ሞት ፡ ፍርዱ ፡ ይህ ፡ ነውና ። ይኸውም ፡ ከልጆቻቸው ፡ ሞት ፡ በፊት ፡ የአባቶች ፡ ሞት ፡ ነው ።

፩ሺ፰፻፶፫ ምዕራፍ ፡ ስለኤጲስቆጶሳትና ፡ ስለመነኰሳት ፡ ርስት ፡ ይናገራል ። የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገንዘብ፡ ከኤጲስቆጶስ ፡ ገንዘብ ፡ የታወቀና ፡ የተለየ ፡ ይሁን ። ገንዘቡ ፡ ለወራሾቹ ፡ ይጠበቅ ፡ ዘንድ ፡ ለወደደውም ፡ ያወርሰው ፡ ዘንድ ። የቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይጠበቅ ፡ ዘንድ ። በኤጲስቆጶስነቱ ፡ ምክንያት ፡ ያገኘው፡ ገንዘብም ፡ ሁሉ ፡ እርሱ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይሁን ። ሊያዝዝበትም ፡ አይገባውም ። የርሱ ፡ ሰዎችም ፡ ሊወርሱ ፡ አይገባም ። ከኤጲስቆጶስነቱ ፡ አስቀድሞ ፡ ያገኘው ፡ ሁሉ ፡ ወይም ፡ ከሆነለት ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ የተራባው ፡ በኤጲስ

አንቀጽ ፡ ተዋርሶ ።

ዘከመ ፡ ተዋርሶ ፡ እው ፡ በጽሒፈ ፡ ትእዛዝ ፡ ይደልዎ ፡ ከመ ፡ የእዝዝ ፡ ቦቱ ፡ ለዘፈቀደ ፡ ወእመእኮሰ ፡ ይተርፍ ፡ ውእቱ ፡ ለወራስያኒሁ ። ወለእመ ፡ እልቦቱ ፡ ምንትኒ ፡ ዘእጥረየ ፡ ይኩን፡ ሲሳዮሙ ፡ ለእለ ፡ ተጸነሱ ፡ እምስብእ ፡ ዚእሁ ፡ እምዘኅደገ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ።

፩ሺ፰፻፶፩ ወለመነኰስኒ ፡ ኢይረሶ ፡ መኑሂ ፡ እምሕዝባውያን ፡ እላ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘኢተርፈ ፡ እምእዝማዲሁ ፡ ለዘሞተ ፡ ዘእንበሌሁ ። ወኢይረስ ፡ ፩ዱሂ ፡ እምሕዝባውያን ፡ ዘእንበለ ፡ ዳእሙ ፡ እምእዝማዲሁ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ እልቦ ፡ ተሳትፎት ፡ ማእከሌሁ ፡ ወማእከለ ፡ ፩ዱ ፡ እመነኰሳት፡ በሕይወተ ፡ ምንኵስና ፡ ወምስለ ፡ እለ ፡ የኀድሩ ፡ ውስተ ፡ ምኔታት ። ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ማእከሌሁ ፡ ወማእከለ ፡ መነኰሳተ ፡ ምኔት ፡ ሱታፌ ውስተ ፡ ሕይወት ፡ ምንኵስናዊት ፡ ወኅድረተ፡ ምኔታት ፡ ይኩን ፡ ኵሉ ፡ ንዋዩ ፡ ለማኅበሮሙ ፡ እመሂ ፡ በዝኁ ፡ ወእመኒ ፡ ውኅዱ ።

፩ሺ፰፻፶፪ ወለእመሂ ፡ ሞተ ፡ በእፍአ ፡ እምኔቶሙ ፡ ወሶበኒ ፡ ቦቱ ፡ ወራሲ ፡ መነኰስ ፡ በእፍእ ፡ እማኅበሮሙ ፡ ወእመኒ ፡ ሀለወ ፡ ውስተ ፡ ማኅበሮሙ ፡ ኢይደልዎ ፡ ለባሕቲቱ ፡ ዘእንበሌሆሙ ። ወለእመ ፡ ተረክበ ፡ ሎቱ ፡ ንዋይ ፡ ዘኅደገ ፡ በእፍእ ፡ እምኔት ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘእዘዘ ፡ ቦቱ ፡ ለምኔት ፡ በኵለንታሁ ፡ እው ፡ በመንፈቁ ፡ በጊዜ ፡ ምንኵስናሁ ፡ እው ፡ እምድኅሬሆሙ ፡ ይቁም ፡ ትእዛዙ ።

፩ሺ፰፻፶፫ ወለዘሰ ፡ ኢእዘዘ ፡ ሎቱ ፡ እምዘይትረከብ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ለእመ ፡ ቦቱ ፡ ወራሲ ፡ ጠባይዓዊ ፡ ይረስ ፡ ኪያሁ ፡ እመሂ ፡ ኮነ ፡ መነኮስ ፡ እው ፡ ሕዝባዊ፡ ወእመ ፡ እኮሰ ፡ ይረስዎ ፡ ማኅበረ ፡ ዚእሁ ። ወእመኒ ፡ ኮነ ፡ ባሕቲቱ ፡ ይነብር ፡ በውስተ ፡ ምኔት ፡ እው ፡ በውስተ ፡ በዓት ወቦቱ ፡ ወራሲ ፡ መነኰስ ፡ እምእዝማዲሁ ፡ ይረሶ ፡ ኪያሁ ። ወእመ ፡ እኮሰ ፡ ይረስዎ ፡ ማኅበረ ፡ መነኰሳት ፡ እለ ፡ ይትራድእዎ ።

፩ሺ፰፻፶፬ ወእልቦቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ለመነኮስ ፡ ዘይነብር ፡ ውስተ ፡ ማኅበር ፡ በተፈልጦ ፡ እምነ ፡ ኵሎሙ ፡ ወትእዛዙሰ ፡ ለመነኰስ ፡ ዘባሕቲቱ ፡ ይነብር ፡ ይቁም ፡ በውሳኔ ፡ ትእዛዝ ፡ ዘእዘዘ ።

፩ሺ፰፻፶፭ ምዕራፍ ፡ በእንተ ፡ ተዋርሶቶሙ ፡ ለግዑዛን፡

የመወራረስ ፡ አንቀጽ ።

ቅጽስነቱ ፡ ምክንያት ፡ አይደለም ። ይኸውም ፡ እንደ ፡ ውርስ ፡ ወይም ፡ በጽሑፍ ፡ እንደታዘዘለት ፡ ያለ ፡ ነው ። ለወደደው ፡ ሊያዝዝበት ፡ ይገባዋል ። ያለዚያ ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ ለወራሾቹ ፡ ይቀራል ። ምንም ፡ ገንዘብ ፡ ያደረገው ፡ ባይኖረው ፡ ከእርሱ ፡ ሰዎች ፡ ወገን ፡ ለተቸገሩት ፡ ምግባቸው ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከተወው ፡ ገንዘብ ፡ ይሁን ።

፩ሺ፰፻፶፩ መነኩሴንም ፡ ከሕዝባውያን ፡ ወገን ፡ ማንም አይውረሰው ። ለሟቹ ፡ ከዘመዶቹ ፡ ወገን ፡ ከእርሱ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ያልቀረ ፡ ቢሆን ፡ ነው ፡ እንጂ ። በምንኵስና ፡ አኗኗርና ፡ በገዳም ፡ ከሚኖሩ ፡ መነኰሳት ፡ ጋራ ፡ በእርሱና ፡ ከመነኰሳት ፡ በአንዱ ፡ መካከል ፡ አንድነት ፡ የሌለው ፡ ቢሆን ፡ ከዘመዶቹ ፡ ወገን ፡ እንጂ ፡ ከሕዝባውያን ፡ አንዱ ፡ አይውረሰው ። በምንኵስና ፡ አኗኗርና ፡ በገዳም ፡ አስተዳደር ፡ በእርሱና ፡ በገዳሙ ፡ መነኰሳት ፡ መካከል ፡ አንድነት ፡ ያለው ፡ ቢሆን ፡ ገንዘቡ ፡ ሁሉ ፡ ቢበዙም ፡ ቢያንሱም ፡ ለማኅበራቸው ፡ ይሁን ።

፩ሺ፰፻፶፪ ከገዳማቸው ፡ በአፍአ ፡ (በውጭ) ፡ ቢሞትም ከማኅበራቸው ፡ በአፍአ ፡ ወይም ፡ በማኅበራቸው ውስጥ ፡ ያለ ፡ ወራሽ ፡ መነኵሴ ፡ ቢኖረውም ፡ ያለእነርሱ ፡ ለብቻው ፡ አይገባውም ። ከገዳሙ ፡ በአፍአ ፡ የተወው ፡ ገንዘብም ፡ ቢገኝለት ፡ በምንኵስናው ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ከምንኵስናው ፡ በኋላ ፡ በመላው ፡ ወይም ፡ በእኩሌታው ፡ ለገዳሙ ፡ ያዘዘበት ፡ ቢሆን ፡ ትእዛዙ ፡ ይጽና ።

፩ሺ፰፻፶፫ በዓለም ፡ ውስጥ ፡ በተገኘ ፡ ገንዘቡ ፡ ያላዘዘበትን ፡ ግን ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ ወራሽ ፡ ቢኖረው ፡ እርሱን ፡ ይውረሰው ። መነኵሴ ፡ ወይም ፡ ሕዝባዊ ፡ ቢሆን ፡ ያለዚያ ፡ ግን ፡ ማኅበሩ ፡ ይውረሱት ። በገዳም ፡ ወይም ፡ በዋሻ ፡ ብቻውን ፡ የሚኖር ፡ ከሆነም ፡ ከዘመዶቹም ፡ ወገን ፡ ወራሽ ፡ መነኵሴ ፡ ቢኖረው ፡ እርሱን ፡ ይውረሰው ። ያለዚያ ፡ ግን ፡ የሚረዱት ፡ የመነኰሳት ፡ ማኅበር ፡ ይውረሱት ።

፩ሺ፰፻፶፬ በማኅበር ፡ ውስጥ ፡ የሚኖር ፡ መነኵሴ ፡ ከሁሉ ፡ በመለየት ፡ ትእዛዝ ፡ የለውም ። ብቻውን ፡ የሚኖር ፡ የመነኵሴ ፡ ትእዛዝ ፡ ግን ፡ በውሳኔ ፡ ያዘዘው ፡ ትእዛዝ ፡ ይጽና ።

፩ሺ፰፻፶፭ ምዕራፍ ፡ ነፃ ፡ ስለወጡና ፡ ስላልወጡ ፡

ወለአግብርት ። ለገብርሰ ፡ ዘተግዕዘ ፡ ይረስዎ ፡
አግዓዝያኒሁ ፡ ወይቀም ፡ ጽሒፈ ፡ ትእዛዙ ፡
ወይረሱ ፡ ርስታቲሁ ፡ ዘከመ ፡ አግዓዝያን ።
ወለእመ ፡ ቦቱ ፡ ወራስያን ፡ ይከውን ፡ ራብዕተ፡
ንዋዩ ፡ ለዘአግዓዞ ፡ ወለእመኒ ፡ ኢአዘዘ ፡ በእን
ቲአሁ ፡ ሎቱ ፡ ለእግዚኡ ፡ ርብዕ ፡ ርስቱ ። ወለ
እመ ፡ አልቦቱ ፡ ወራስያን ፡ ወኢጽሒፈ ፡ ትእ
ዛዝ ፡ ኵሉ ፡ ርስቱ ፡ ዘንዩግ ፡ ይኩን ፡ ለእግዚኡ

፩ሺ፰፻፶፱ ወለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘአግዓዞ ፡ ፩ዱ ፡ አው ፡ ዘይ
በዝኅ ፡ እምዕዱ ፡ በአምጣነ ፡ ዘአግዓዞ ፡ እም
ኔሁ ። ወእምድኅረ ፡ ግዑዝ ፡ ይረሱ ፡ ሰብኡ ፡
ወለእመ ፡ ኢተረክበ ፡ ይኩን ፡ በከመ ፡ ፍትሑ ፡
ለዘአግዓዞ ፡ ለግዑዝ ።

፩ሺ፰፻፷ ወገብርኒ ፡ ኢይረስ ፡ ዘእንበለ ፡ በጽሒፈ ፡ ትእ
ዛዝ ፡ እምነ ፡ መዋቲ ፡ ወኢይረስ ፡ ዘእንበለ ፡
እግዚኡ ፡ ወእመኒ ፡ ቦቱ ፡ ወልድ ፡ አው ፡ አብ ፡
አው ፡ አዝማድ ፡ ወእመኒ ፡ አግዓዝያን ፡ እሙ
ንቱ ። እስመ ፡ ኵሉ ፡ ዘይመልክ ፡ ገብር ፡ ውእቱ
ምልከተ ፡ እግዚኡ ፡ ወበእንተዝ ፡ አልቦቱ ፡
ጽሒፈ ፡ ትእዛዝ

፩ሺ፰፻፷፩ ምዕራፍ ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ኢይወርሱ ፡ ዘእን
በለ ፡ በጽሒፈ ፡ ትእዛዝ ፡ ወውእቶሙ ፡ ፪ቱ ፡
አክፋል ። ቀዳማዊ ፡ እሙንቱ ፡ እለ ፡ አልቦ ፡
ማእከሌሆሙ ፡ ወማእከለ ፡ ምዉት ፡ ተዋስ
ቦት ፡ ወኢተዘምዶት ፡ ጠባይዓዊ ፡ ወእመኒ ፡
ኮነ ፡ ማእከሌሆሙ ፡ ተዘምዶ ፡ ዘንባሬ ፡ አው ፡
ዘአስተዋስቦ ። '

፩ሺ፰፻፷፪ ወዳግማዊ ፡ ክፍል ፡ እሙንቱ ፡ ደቂቅ ፡ ወዘ
መድ ፡ እለ ፡ ተወልዱ ፡ በተዋስቦ ፡ እንተ ፡ ኢኮ
ነት ፡ ዘበሕግ ፡ ወአግብርትኒ ፡ ወዘማውያን ፡
እለ ፡ ዘመዉ ፡ በብእሲተ ፡ ዘይትወረስ ፡ አው ፡
በወለቱ ፡ አው ፡ በእኅቱ ፡ አው ፡ በእሙ ። ወእለ
ያስተዋድይዎ ፡ በዘያጠፍኡ ፡ ንዋዮ ፡ ወእለ ፡
ይትመከነዩ ፡ በእጥፍአተ ፡ ልቡ ፡ ወእለሂ ፡ ይት
ሄየዩ ፡ መድኃኔቶ ፡ ለዘተሞቅሐ ፡ እንዘ ፡ ይት
ከሀሎሙ ፡ ለሐዊር ፡ ከመ ፡ ያድኅንዎ ፡ ኢይረ
ስዎ ፡ ዘእንበለ ፡ ጽሒፈ ፡ ትእዛዝ ፡ ዘጸሐፈ ፡
እምድኅረ ፡ ተሞቅሖቱ ።

፩ሺ፰፻፷፫ ወወልድሰ ፡ ዘአሕሠመ ፡ ላዕለ ፡ አቡሁ ፡
እመሂ ፡ ዘይዘብጦ ፡ ለአቡሁ ፡ ወዘሂ ፡ ዘልፈ ፡
ይጼእሎ ፡ አው ፡ ዘያጠፍእ ፡ ንዋዮ ፡ በውዴት ፡



ባሮች ፡ አወራረስ ፡ ይናገራል ። ነፃ ፡ የወጣ ፡
ባሪያን ፡ ነፃ ፡ ያወጡት ፡ ጌቶቹ ፡ ይውረሱት ።
የትእዛዙ ፡ ደብዳቤም ፡ ይጽና ። ነፃ ፡ አውጭ
ዎች ፡ ጌቶች ፡ እንደመሆናቸው ፡ ርስቶቹን ፡
ይውረሱ ። ወራሾች ፡ ቢኖሩትም ፡ የገንዘቡ ፡
አንድ ፡ አራተኛው ፡ ለጌታው ፡ ገንዘቡ ፡ ነው ።
ወራሾች ፡ ወይም ፡ የትእዛዝ ፡ ደብዳቤ ፡ ባይኖ
ረው ፡ የተወው ፡ ርስቱ ፡ ሁሉ ፡ ለጌታው ፡
ይሁን ።

፩ሺ፰፻፶፱ ነፃ ፡ ያወጣው ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ከአንድ ፡
የሚበዛ ፡ ቢሆን ፡ ከእርሱ ፡ ነፃ ፡ በአወጣው ፡
መጠን ፡ ልክ ፡ ነው ። ከነፃ ፡ አውጭውም ፡ ቀጥ
ለው ፡ ሰዎቹ ፡ ይውረሱ ፡ (ወራሽ) ፡ ባይገኝም ፡
ነፃ ፡ የወጣውን ፡ ነፃ ፡ እንደአወጣው ፡ ሰው ፡
ፍርድ ፡ ይሁን ።

፩ሺ፰፻፷ ነፃ ፡ ያልወጣ ፡ ባሪያም ፡ ከሟች ፡ በጽሕፈት
ካልታዘዘለት ፡ በቀር ፡ አይውረስ ። ከጌታውም፡
በቀር ፡ ሌላ ፡ አይውረሰው ። ልጅ ፡ ወይም ፡
አባት ፡ ወይም ፡ ዘመድ ፡ ቢኖረውም ፡ ነፃ ፡
የወጡ ፡ ቢሆኑም ፡ ባሪያው ፡ ገንዘብ ፡ የሚያደር
ገው ፡ ሁሉ ፡ የጌታው ፡ ገንዘብ ፡ ነውና ። ስለ
ዚህ ፡ ትእዛዝ ፡ መጻፍ ፡ የለበትም ።

፩ሺ፰፻፷፩ ምዕራፍ ፡ ያለማዘዣ ፡ ደብዳቤ ፡ ስለማይወ
ርሱ ፡ ሰዎች ፡ ይናገራል ። እነዚህም ፡ ሁለት ፡
ክፍሎች ፡ ናቸው ። አንደኛው ፡ በእነርሱና ፡
በሟች ፡ መካከል ፡ ጋብቻ ፡ ወይም ፡ ሥጋዊ ፡
ተዘምዶ ፡ የሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ አብሮ ፡ የመ
ኖር ፡ ወይም ፡ የማጋባት ፡ ተዘምዶ ፡ በመካከ
ላቸው ፡ ቢኖርም ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

፩ሺ፰፻፷፪ ሁለተኛውም ፡ ክፍል ፡ በሕግ ፡ ባልሆነች ፡
ጋብቻ ፡ የተወለዱ ፡ ልጆችና ፡ ዘመዶች ፡ ባሮች
ም ፡ በተወራሽ ፡ ሰው ፡ ሚስት ፡ ወይም ፡ በሴት ፡
ልጁ ፡ ወይም ፡ በእኅቱ ፡ ወይም ፡ በእናቱ ፡ ያመ
ነዘሩ ፡ ዘማውያን ፡ ገንዘቡንም ፡ በሚያጠፉ ፡
ሁናቴ ፡ ነገር ፡ የሚሠሩ ፡ አእምሮዉንም ፡ ለማ
ጥፋት ፡ ምክንያት ፡ የሚያደርጉ ፡ የታሰረው
ንም ፡ ያድኑት ፡ ዘንድ ፡ ለመሄድ ፡ ሲቻላቸው ፡
መድኃኒቱን ፡ ቸል ፡ የሚሉት ፡ ከመታሰሩ ፡
በኋላ ፡ ከጻፈው ፡ ከትእዛዝ ፡ ደብዳቤ ፡ በቀር ፡
አይውረሱት ።

፩ሺ፰፻፷፫ በአባቱ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ የሠራ ፡ ልጅ ፡ አባቱን ፡
የሚመታውም ፡ ዘወትር ፡ የሚሰድበውም ፡
ወይም ፡ በክፉ ፡ ነገር ፡ ሥራ ፡ ገንዘቡን ፡ የሚያ

አንቀጸ ፡ ተዋርሶ ።

ሐሡም ፡ እው ፡ ዘይከልኦ ፡ በግብር ፡ እምገ
ቢረ ፡ ትእዛዝ ፡ እው ፡ ዘኢያስተሐምም ፡ በጊዜ፡
ምንዳቤሁ ፡ በእምጣነ ፡ ክሂሎቱ ፡ እው ፡ ዘይ
ዴመር ፡ ምስለ ፡ ገባርያነ ፡ እከይ ፡ ወእለ ፡ የሐ
ውሩ ፡ በእኩይ ፡ ለአሕሥሞተ ፡ ወላድያኒሆሙ ፡
እው ፡ ዘይፈልስ ፡ ኀበ ፡ ዘኢኮነ ፡ ሕዝበ ፡
ዚእሁ ፡ ለይስድዶ ፡ አቡሁ ፡ እምርስተ ፡ ዚእሁ
ወእመሰ ፡ ሰደዶ ፡ ዘእንበለ ፡ ዕዳ ፡ ይንሣእ ፡
ወልዱ ፡ መክፈልተ ፡ ዚእሁ ፡ ራብዕተ ፡ እድ ፡
እምርስተ ፡ አቡሁ ፡ እው ፡ ዅለንታሁ ፡ ለእመ ፡
አልቦቱ ፡ ካልእ ፡ ዘእንበሌሁ ።

፩ሺ፰፻፷፩ ወከማሁ ፡ ግብረ ፡ ብእሲትኒ ፡ እምርስቱ ፡
እው ፡ ደኅራ ፡ በኀበ ፡ ዘኢኮነ ፡ ግብረ ፡ ዚእሃ ፡
ኢይትወከፉ ፡ እምኔሁ ፡ ዘንተ ፡ ውስተ ፡ ራብ
ዕተ ፡ እድ ፡ ለግሙራ ፡ ወእመኒ ፡ ከመ ፡ ይትካ
ፈል ፡ ምስለ ፡ ወራስያን ። ወከማሁ ፡ ለእመ ፡
ፈቀደ ፡ ከመ ፡ ያስተዋስባ ፡ ለወለቱ ፡ እው ፡
ለወለተ ፡ ወልዱ ፡ ወእበየት ፡ ፈቂዳ ፡ ሐዊረ ፡
ኀበ ፡ ገቢረ ፡ ኀፍረት ።

፩ሺ፰፻፷፪ ምዕራፍ ፡ በእንተ ፡ ዘኢይወርስ ፡ ወእመሂ ፡
ጸሐፈ ፡ ሎቱ ፡ ትእዛዘ ፡ ወለዘየእምንሂ ፡ ኢይ
ረሶ ፡ ዘኢየእምን ፡ ዘእንበለ ፡ ዳእሙ ፡ ለእመ ፡
ተጠየቀ ፡ ግብአቱ ፡ ኀበ ፡ ሃይማኖት ፡ እምቅ
ድመ ፡ ይትፈለጥ ፡ ተከፍሎቱ ፡ ለንዋየ ፡ ርስት፡
ዘኀደገ ። ወቀታሊሁሰ ፡ ለዘይወርሶ ፡ ወአግ
ባኢሁኒ ፡ ለዘይቀትሎ ፡ ወዘያስተሐምም ፡ ለአ
ማስኖተ ፡ ሕይወቱ ፡ በአብልዮ ፡ ሕምዝ ፡ እው፡
በካልእ ፡ ዘእንበለ ፡ ዳእሙ ፡ ለእመ ፡ ኮነ ፡ ዘአ
ዘዘ ፡ እምድኅረ ፡ ዝንቱ ።

፩ሺ፰፻፷፫ ምዕራፍ ፡ በእንተ ፡ ዘይትዓቀፉ ፡ ቦቱ ፡ ወው
እቱ ፡ ፪ቱ ፡ እክፉል ። ፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ለእመ
ሞቱ ፡ እምወራስያን ፡ ፪ቱ ፡ እው ፡ ዘይበዝኁ ፡
በንግደት ፡ እው ፡ በተሠጥሞ ፡ እው ፡ በውዕ
የተ ፡ እሳት ፡ እው ፡ በድቀተ ፡ ቤት ፡ ላዕሌ
ሆሙ ፡ ወፈድፋደሰ ፡ ለእመ ፡ ኢተዐውቀ ፡
መኑ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘተርፈ ፡ እምድኅረ ፡ ካልኡ
ኢይወርሶ ፡ ፩ዱ ፡ ለካልኡ ፡ ወኢይወርሶ ፡ ለለ
፩ዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘይደልዎ ፡ ርስተ ፡
ዚእሁ ፡ እምነ ፡ ሕያዋን ፡ ወእኮ ፡ እምነ ፡ ምዉ
ታን ፡ እለ ፡ ኢይትዐወቅ ፡ ግብሮሙ ፡ በእቅ
ድሞ ፡ ወበእስተድኅሮ ።

የመወራረስ ፡ አንቀጽ ።

ጠፉ ፡ ወይም ፡ ትእዛዝ ፡ ከማድረግ ፡ ወገን ፡
በግድ ፡ የሚከለከለው ፡ ወይም ፡ በችግሩ ፡ ጊዜ ፡
በተቻለው ፡ መጠን ፡ የማያስብ ፡ ወይም ፡
ከክፉ ፡ አድራጎትና ፡ በወላጆቻቸው ፡ ክፉ ፡
ለማድረግ ፡ በክፋት ፡ ከሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡
የሚተባበር ፡ ወይም ፡ ሌጋው ፡ (ወገኑ) ፡ ወደ ፡
አይደለ ፡ ሌጋ ፡ (ወገን) ፡ የሚለወጥ ፡ ቢሆን ፡
አባቱ ፡ ከርስቱ ፡ ይንቀለው ፡ (ያባርረው) ። ያለ
በደል ፡ ቢያባርረው ፡ ግን ፡ ከእርሱ ፡ በቀር ፡
ሌላ ፡ ከሌለው ፡ ከአባቱ ፡ ርስት ፡ አራቸኛውን ፡
እጅ ፡ ወይም ፡ መላውን ፡ ድርሻውን ፡ ልጁ ፡
ይውሰድ ።

፩ሺ፰፻፷፩ የሚሰትም ፡ ነገር ፡ ከርስቱ ፡ እንደዚሁ ፡
ነው ። ሥራዋ ፡ በአልሆነ ፡ ነገር ፡ ቢፈታትም ፡
ከወራሾች ፡ ጋራ ፡ እንዲከፈል ፡ ቢሆንም ፡
ከቶ ፡ በአራተኛው ፡ እጅ ፡ ውስጥ ፡ ይሀን ፡ ከእ
ርሱ ፡ አይቀበሉ ። (ከአራት ፡ አንድ ፡ አትጣ) ፡
ሴት ፡ ልጁን ፡ ወይም ፡ የወንድ ፡ ሴት ፡ ልጁን ፡
ሊያገባት ፡ ቢወድ ፡ ወደሚያሳፍር ፡ ሥራ ፡
መሄድን ፡ ፈቅዳ ፡ እንቢ ፡ ብትል ፡ እንደዚሁ ፡
ነው ።

፩ሺ፰፻፷፪ ምዕራፍ ፡ ስለማይወርስ ፡ ይናገራል ። ትእ
ዛዝ ፡ ቢጽፍለትም ፡ የማያምን ፡ የሚያምነ
ውን ፡ አይውረሰው ። ሙዋች ፡ የተወው ፡ የር
ስት ፡ ሀብት ፡ ከመከፈሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ወደሃይ
ማኖት ፡ መመለሱ ፡ ቢረጋገጥ ፡ ነው ፡ እንጂ ።
ተወራሹን ፡ የገደለ ፡ ግን ፡ ለሚገድለውም ፡ አሳ
ልፎ ፡ የሰጠው ፡ መርዝ ፡ በማብላት ፡ ወይም ፡
በሌላ ፡ ሕይወቱን ፡ ለማጥፋት ፡ የሚጣጣር ፡
ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያዘዘለት ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ።

፩ሺ፰፻፷፫ ምዕራፍ ፡ ስለሚሰናከሉበት ፡ ይናገራል ።
ይኸውም ፡ ሁለት ፡ ክፍል ፡ ነው ። ከእነርሱም ፡
አንዱ ፡ ከወራሾች ፡ ሁለቱ ፡ ወይም ፡ ብዙዎች ፡
ዕሩቅ ፡ በመሄድ ፡ ወይም ፡ በመስጠም ፡ ወይም፡
በእሳት ፡ በመቃጠል ፡ ወይም ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡
በቤት ፡ መናድ ፡ ቢሞቱ ፡ ይልቁንም ፡ ከእነርሱ
ከሌላው ፡ በኋላ ፡ ማን ፡ እንደቀረ ፡ ባይታወቅ ፡
አንዱ ፡ ሌላውን ፡ አይወርሰውም ። ከእነርሱ ፡
ለእያንዳንዳቸው ፡ በመቅደምና ፡ በመከታተል ፡
ግብራቸው ፡ ካልታወቀ ፡ ከሙታን ፡ ወገን ፡
ያይደለ ፡ ከሕያዋን ፡ ወገን ፡ ከሚገባው ፡ ውርሱ
በቀር ፡ አይወርሰውም ።

## አንቀጸ ፡ ተዋርሶ ።

፩ሺ፰፻፹፯ ወካልእኒ ፡ ክፍል ፡ ዘይክልእ ፡ እምነ ፡ አስተ ዋፅኦ ፡ በግብር ፡ በአንተ ፡ ኑፋቄ ፡ ሕሊና ፡ በተ ኃጥኦቶሙ ፡ ለዘተሞቅሐሂ ፡ ወለዘነገደ ፡ ወፈደ ፋደስ ፡ ለዘተኀጥአ ፡ ዜናሁ ፡ ኢይክፍሉ ፡ ንዋዮ ለዘሀለወ ፡ ለእመ ፡ ኢተጠየቀ ፡ ሞተ ፡ ዚአሁ ። ወለእመ ፡ ኢኀለፈ ፡ ዕድሜ ፡ ተኃጥአቱ ፡ በፍ ትሐ ፡ መኰንን ፡ ከመ ፡ ዘከማሁ ፡ ኢየሐዩ ፡ ባቲ ። ወእመኒ ፡ ሞተ ፡ ወሎቱ ፡ ዘመድ ፡ ዘሀ ልው ፡ ይረስዩ ፡ ክፍለ ፡ ዚአሁ ፡ በተዓቅቦ ፡ ወያ ንብሩ ፡ ንዋዮ ፡ ማኅፀንተ ፡ እስከ ፡ ይትፈታሕ ፡ በእንቲአሁ ፡ በአእምሮ ፡ ወበልባዌ ፡ በዘይደሉ፡ ክዊነ ፡ አምሳሊሁ ።

፩ሺ፰፻፹፰ መልአ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፈ ፡ ቀኖና ፡ ዘፍ ትሐ ፡ ዘነኔ ፡ ሕግ ፡ መሢሐዊት ፡ ወዘአዕለዋ ፡ ሕጹጽ ፡ ወኃጥእ ፡ ብዙኃ ፡ አበሳ ፡ ዘኢይደልዎ ፡ ከመ ፡ ይሰመይ ፡ ሰብአ ፡ ወፈድፋደሰ ፡ ከመ ፡ ይስመይ ፡ ዲያቆነ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወልደ ፡ ዐብደልሰይ ይድ ፡ እምዘ ፡ አስተሐመመ ፡ በዝንቱ ፡ ቀሲስ ፡ ክቡር ፡ ትሩፈ ፡ ምግባር ፡ ብፁዓዊ ፡ አብርሃም ፡ ወልደ ፡ ሐናናዋያን ፡ እግዚአብሔር ፡ ያፈድ ፍድ ፡ ዓስቦ ። ወአዕሳዊሃኒ ፡ ስኡን ፡ ወአባሲ ፡ ይስእሎ ፡ ለኵሉ ፡ ዘያነብባ ፡ ለዛቲ ፡ መጽሐፍ ፡ ከመ ፡ ያስተሣኒ ፡ ዘተረክበ ፡ ግድፈተ ፡ ቃል ፡ እስመ ፡ አነ ፡ አአምር ፡ ከመ ፡ ሕጹጸ ፡ አእምሮ፡ አነ ፡ ወስኡን ፡ ወይስእል ፡ ሊተ ፡ ሥርየተ ። ወዘሂ ፡ ስአለ ፡ ሊተ ፡ በምንትኒ ፡ ቦቱ ፡ ምክዕ ቢት ፡ በአምሳለ ፡ ዝንቱ ።

፩ሺ፰፻፹፱ ወንስእሎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ያስም ዓነ ፡ ለኵልነ ፡ ቃለ ፡ ፍሥሓ ፡ ንዑ ፡ ኅቤየ ፡ ቡሩካኑ ፡ ለአቡየ ፡ ትረሱ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማ ያት ፡ ዘተደለወ ፡ ለክሙ ፡ እምቅድመ ፡ ይትፈ ጠር ፡ ዓለም ፡ ወይሥረይ ፡ ኃጢአተነ ፡ ወዳ ኅፃቲነ ። ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወትረ ፡ እስከ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ ወላዕሌነ ፡ ትኩን ፡ ምሕረቱ ፡ አሜን ፡ ወአሜን ።

፩ሺ፰፻፺ ተፈጸመት ፡ ዛቲ ፡ መጽሐፍ ፡ ከመ ፡ ያእምሩ ፡ ባቲ ፡ ኵሎሙ ፡ ሰብአ ፡ ምእመናን ፡ ሥርዓተ ፡ ቀኖና ፡ ዘቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅድስት ፡ መንፈሳ ዊት ፡ ወሥርዓተ ፡ ኵነኔ ፡ ሥጋዊት ፡ ንጉሣ

## የመወራረስ ፡ አንቀጽ ።

፩ሺ፰፻፹፯ ሁለተኛውም ፡ ክፍል ፡ ገንዘቡን ፡ በግድ ፡ ከማወጣጣት ፡ የሚከለክል ፡ ነው ። የታሰረና ፡ ዕሩቅ ፡ ሀገር ፡ የሄደ ፡ ይልቁንም ፡ ወሬው ፡ የጠፋ ፡ ሰው ፡ በመታጣታቸው ፡ ስለሕሊና ፡ ጥርጥር ፡ ሞቱ ፡ ካልተረጋገጠ ፡ ገንዘቡን ፡ (በሕይወት) ፡ ለአለ ፡ ሰው ፡ አይከፈሉ ። የመ ታጣቱ ፡ ዘመን ፡ ባያልፍም ፡ እንደእርሱ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ እንደማይኖርባት ፡ በዳኛ ፡ ፍርድ ፡ ነው ። ቢሞትም ፡ በሕይወት ፡ ያለ ፡ ዘመድ ፡ ቢኖረ ውም ፡ ፈንታውን ፡ በጥንቃቄ ፡ ያድርጉ ። ገን ዘቡንም ፡ የምሳሌው ፡ ሁኔታ ፡ በሚገባ ፡ ገን ዘብ ፡ በዕውቀትና ፡ በማስተዋል ፡ ስለእርሱ ፡ እስኪፈረድ ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ አደራ ፡ ያኑሩ ።

፩ሺ፰፻፹፰ ክርስቶሳዊት ፡ ከሆነች ፡ ከሕግ ፡ የቅጣት ፡ ፍርድ ፡ የተገኘ ፡ ይህ ፡ የትእዛዝ ፡ መጽሐፍ ፡ መላ ። (ተፈጸመ) ። የተረጐማትም ፡ ታናሽና ፡ ኃጢአተኛ ፡ በደሉ ፡ የበዛ ፡ ሰው ፡ ሊባል ፡ ይል ቁንም ፡ ዲያቆን ፡ ሊባል ፡ የማይገባው ፡ የአብ ደል ፡ ሰይድ ፡ ልጅ ፡ ጴጥሮስ ፡ ነው ። እግዚአብ ሔር ፡ ዋጋውን ፡ ያብዛለትና ፡ ምግባሩ ፡ የበዛ ፡ ብፁዕ ፡ የሆነ ፡ የሐናናዋያን ፡ ልጅ ፡ ክቡር ፡ ቄስ ፡ አብርሃም ፡ በዚህ ፡ ከደከመበት ፡ በኋላ ፡ ደካማ ፡ በደለኛ ፡ የሚሆን ፡ ተርጓሚዋም ፡ ይችን ፡ መጽሐፍ ፡ የሚያነብባትን ፡ ሁሉ ፡ የተ ገኘውን ፡ የቃሏ ፡ ግድፈት ፡ እንዲያቃና ፡ ይለ ምነዋል ። እኔ ፡ አእምሮ ፡ ያነሰኝ ፡ ደካማም ፡ እንደሆንሁ ፡ አውቃለሁና ። ይቅርታንም ፡ ይለ ምንልኝ ። በማናቸውም ፡ ለእኔ ፡ የለመነ ፡ ሰውም ፡ ለእርሱም ፡ በዚህ ፡ አምሳል ፡ ዕጽፍ ፡ ድርብ ፡ አለው ።

፩ሺ፰፻፹፱ ለሁላችንም ፡ የአባቴ ፡ ቡሩካን ፡ ዓለም ፡ ሳይ ፈጠር ፡ የተዘጋጀላችሁ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያ ትን ፡ ትወርሱ ፡ ዘንድ ፡ ወደእኔ ፡ ኑ ፡ የሚል ፡ የደስታ ፡ ቃልን ፡ ያሰማን ፡ ዘንድ ፡ ኃጢአታች ንና ፡ ስሕተታችንንም ፡ ይቅር ፡ ይለን ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንለምነው ። ለእግዚአብሔር ም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ። ይቅርታውም ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ ትሁን ። አሜን ።

፩ሺ፰፻፺ ይች ፡ መጽሐፍ ፡ ምእመናን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ መንፈሳዊት ፡ የሆነች ፡ የቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክር ስቲያን ፡ የፍርድ ፡ ሥርዓትንና ፡ ንጉሥ ፡ የሚፈ ርዳት ፡ የሥጋዊት ፡ ቅጣት ፡ ሥርዓትን ፡ ያውቁ ባት ፡ ዘንድ ፡ ከብሉይ ፡ ከሐዲስ ፡ ከትእዛዛት ፡

አንቀጸ ፡ ተዋርሶ ።

ዊት ፡ ዘብሉይ ፡ ወዘሐዲስ ፡ ወዘቀኖናት ፡ ከመ ፡ ትኩኖሙ ፡ ለመድኃኒተ ፡ ነፍስ ፡ ወሥጋ ፡ ወዝ ከረ ፡ ሠናየ ፡ በዝ ፡ ዓለም ፡ ወበዘይመጽእ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

የመወራረስ ፡ አንቀጽ ።

(ከሊቃውንት) ፡ ተወጣጥታ ፡ ተጻፈች ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ በሚመጣውም ፡ የነፍስና ፡ የሥጋ ፡ መድኃኒት ፡ መልካም ፡ መታሰቢያም ፡ ትሆና ቸው ፡ ዘንድ ፡ ለዘለዓለሙ ፡ አሜን ።